ISIC

# የግራኝ አሕመድ ወረራ

ISIC

ከተክለ ጻድቅ መኵሪያ

ያለደራሲው ፈቃድ ይህን መጽሐፍ ማንም ሰው ሊያሳትም አይችልም።

All rights reserved

# መታሰቢያ ለአዝማች አዳሉ ።

ISIC

አዝማች አዳሉ የባሌ ጌታ የእግረኛውን ጦር ከፈረሰኛው ፊት አስቀድመውና እራሱ ላይ ወጥቶ እንደ ብረት ሕንፃ ቆሞ የመካከለኛውን ሥፍራ ያዘ ። ለቤተ ሰቦቹም እንደዚህ አላቸው «ዛሬ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነገር ሥራ የምንሠራበት ታላቅ የተከበረ ቀን ነውና የክት ልብሶቻችሁን ልበሱ ጌጣችሁንም አጊጡ ...» ገጽ ፩፻፴፱ ።

በብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት ታተመ።



ደራሲው

ISIC

## ማውጫ


| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
| --- | --- | --- | --- |
| ፩ኛ | | **በግራኝ አህመድ ወረራ ዋዜማ የኢትዮጵያ ጠቅላላ ሁኔታ** | |
| | ፩ | የአማራ ሕዝብ በይኩኖ አምላክ መሪነት የንጉሥነት ሥልጣን መያዝ | ፩ - ፮ |
| | ፪ | የአማራ ሕዝብ ዘሩና ያለባቸው አውራጃዎች | ፮ - ፲፩ |
| | ፫ | የነገሥታቱ ዘር (እስራኤላዊና ሳባዊ) | ፲፩ - ፲፮ |
| | ፬ | የንጉሠ ነገሥቱ ወሰን የሌለው ሥልጣን | ፲፮ - ፳፩ |
| | ፭ | የዘመኑ መንፈሳዊ ትምህርትና ከሥልጣኔ ጋር ያለው መራራቅ | ፳፩ - ፳፱ |
| | ፮ | የኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ደረጃና የሚገኝባቸው ምንጮች | ፴ - ፴፫ |
| | ፯ | የዘመኑ ጸሐፊና የቀለም[illegible]፡ | ፴፫ - ፵፩ |
| | ፰ | የአገር ሀብት ብዛት — የተዘዋዋሪ ገንዘብ እጦት — | ፵፩ - ፵፯ |
| | ፱ | በዚህ ዘመን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ደረጃ | ፵፯ - ፶፭ |
| ፪ኛ | | **የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ግንኙነት** | |
| | ፲ | በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል ያለው የሃይማኖትና የሥልጣኔ ልዩነት — የፖርቱጋል ኃያልነት በኢትዮጵያ ስለመሰማቱ | ፶፭ - ፷፫ |
| | ፲፩ | የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ግንኙነት ንግሥት ዕሌኒ በማቴዎስ እጅ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ወደ አማኑኤል የላኩት ደብዳቤ | ፷፫ - ፸፪ |
| | ፲፪ | ስለ ዓፄ ልብነ ድንግል | ፸፪ - ፸፱ |
| | ፲፫ | የዓፄ ልብነ ድንግልና የእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋብቻ | ፸፱ - ፹፭ |
| | ፲፬ | ኢትዮጵያ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ግብጽ ፣ የኢትዮጵያ መላክተኞች በካይሮ ፲፭፻፱ ዓ. ም. | ፹፭ - ፺፭ |
| | ፲፭ | ከዓረቦች ወረራ በኋላ የቱርክ የቄሣር መንግሥት ግብፅ በቱርኮች እንደተወረረች — የግብፅ የመጨረሻው ሱልጣን ቱማን በቱርኩ ሱልጣን በሳሊም ትእዛዝ እንደ ሞተ (፲፭፻፲ ዓ. ም.) | ፺፭ - ፺፱ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
| --- | --- | --- | --- |
| | ፲፮ | የማኅፉድና ያፄ ልብነ ድንግል ጦርነት (፲፭፻፳ ዓ. ም.) ስለ አባ ገብረ እንድርያስ | ፻ - ፻፮ |
| | ፲፯ | የፖርቱጋል መልክተኞችና የሕንድ ገዥ ምተቸ መድረስ (፲፭፻፲፪ ዓ. ም.) | ፻፮ - ፻፲፪ |
| | ፲፰ | የፖርቱጋል መልክተኞች ከምጥዋ ወደ ደብረ ሊባኖስ መድረስ — የአልቫሬዝ ሰንብቶም ሸዋ መምጣትና ከንጉሡ ቤተ ብዙ ወደ ግዕዝ የተረጐሟቸው መጻሕፍት | ፻፲፫ - ፻፲፰ |
| | ፲፱ | የፖርቱጊዞቹ ሸዋ መድረስ — ዓፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት የገጠማቸው ቀዝቃዛ መስተንግዶና የረዥም ቀን ደጅ ጥናት (፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ጥቅምት ፱ ቀን) | ፻፲፰ - ፻፳፪ |
| | ፳ | በመጨረሻ ዓፄ ልብነ ድንግል መልክተኞቹን እንደ ተቀበሏቸው (፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ኅዳር ፲፪ ቀን) | ፻፳፫ - ፻፳፭ |
| | ፳፩ | መስተንግዶው የቀዘቀዘበት ልዩ ልዩ ምክንያት | ፻፳፭ - ፻፳፱ |
| | ፳፪ | የንግሥት [illegible]ሥልጣን መውጣት | ፻፴ - ፻፴፪ |
| | ፳፫ | የኢትዮጵያና የፖርቱጋል የተያያዘና የተለየየ ጥቅም | ፻፴፪ - ፻፴፭ |
| | ፳፬ | ፖርቱጋሎቹ በኢትዮጵያ በነበሩበት ሰዓት ከየትና ከሰሙት ውስጥ የዜተ መንግሥታት እርስ በርስ መመራመር (፲፭፻፲፫ - ፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) | ፻፴፭ - ፻፵ |
| | ፳፭ | ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤል የተዘጋጀው ደብዳቤና ገጸ በረከት (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) | ፻፵ - ፻፵፬ |
| | ፳፮ | ስለ ንጉሥ አማኑኤል ዕረፍት — ለዮሐንስ ፫ኛ የተጻፈው ደብዳቤ | ፻፵፬ - ፻፶ |
| ፫ኛ | | የግራኝ አህመድ ወረራ | ፻፶፩ - ፻፶፯ |
| | ፳፯ | የ"በከንቱ ጦር አውርድ" አለመታመን | |
| | ፳፰ | ስለ ግራኝ አህመድ ትውልድና እንግስ ከፋንኢል ጋር ያደረገው የመጀመሪያው ጦርነት (፲፭፻፲፯ ዓ. ም.) | ፻፶፯ - ፻፷፫ |
| | ፳፱ | የግራኝ አህመድ ጕማውና ትውልዱ ከወዴት ነው? | ፻፷፬ - ፻፷፯ |
| | ፴ | በግራኝ አህመድና በሱልጣን አቡበከር መካከል የተደረገው ጦርነት (፲፭፻፲፯ ዓ. ም.) | ፻፷፰ - ፻፸፫ |
| | ፴፩ | ድሉን ያከናወኑለት ዋነኞቹ ምክንያቶች | ፻፸፫ - ፻[illegible] |
| | | | ፻[illegible] - ፻[illegible] |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
| --- | --- | --- | --- |
| | ፷፪ | በአዛዥ ደገልሃንና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገው የመጀመሪያው ጦርነት (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) | ፻፹፱ - ፻፺፬ |
| | ፷፫ | በግራኝና በሹማምንቱ (ኤሚሮቹ) መካከል ጦርነቱን የመተውና የመቀጠል ምክር ከአርባ ሺመልና ከወናግ ዣን ጋር የተደረገው ጦርነት — ድል ወንበራ ለጦርነቱ ቆርጣ እንደተነሣች (፲፭፻፳ ዓ.ም.) | ፻፺፬ - ፻፺፱ |
| | ፷፬ | ግራኝ አህመድ ከሸዋ ወደ ሐረርጌ ሄዶ ወታደር በሚመለምልበት ሰዓት ዓፄ ልብነ ድንግል ከባደቄ ወደ ቤተ አምሐራ ሄደው ለጦርነት እንደተዘጋጁ (፲፭፻፳ - ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) | ፪፻ - ፪፻፯ |
| | ፷፭ | የግራኝ አህመድ ጦር በሰልፍ ወደ ባደቄ ስለ መጓዙ | ፪፻፰ - ፪፻፲፪ |
| | ፷፮ | የባደቄ ጦርነትና ጦርነቱን የተካፈሉት የኢትዮጵያ መኳንንት ቢትወደድ ሠርፄ ሕግዱ ራስ ማኅፀንቶ አውራይ ኡስማን ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ጸሐፊ ላህም ሮቢል (፲፭፻፳፩ ዓ.ም. መስከረም) | ፪፻፲፪ - ፪፻፲፱ |
| | ፷፯ | በአሳብ መለያየትና በስለላ ጉድለት የተነሣ የግራኝ ወረራ መቃናት | ፪፻፳ - ፪፻፳፫ |
| | ፷፰ | በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዋዜማ በሁለቱ ተዋጊዎች ዘንድ የነበረው ሁኔታና የሰልፍ ዝግጅት (መስከረም - መጋቢት ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) | ፪፻፳፬ - ፪፻፳፰ |
| | ፷፱ | በሽምብራ ኩሬ ዓፄ ልብነ ድንግልና ግራኝ አህመድ ያደረጉት ውጊያና የንጉሠ ነገሥቱ መሸነፍ (፲፭፻፳፩ መጋቢት ፲፩ ቀን) | ፪፻፳፰ - ፪፻፴፮ |
| | ፸ | በሽምብራ ኩሬ የሞቱት የጦር አለቆች ዝርዝር የውጊያው አመራርና የተዋጊው ወታደር መጠን | ፪፻፴፬ - ፪፻፴፰ |
| | ፸፩ | በደዋሮ የግራኝና የራስ ነቢያት ጦርነት (፲፭፻፳፪ ዓ. ም.) | ፪፻፵፩ - ፪፻፵፫ |
| | ፸፪ | የሡልጣንና የይማም ልዩነት — የሡልጣን ኡመርዲንና የግራኝ አህመድ ጠብና ዕርቅ (፲፭፻፳፪ ዓ. ም.) | ፪፻፵፫ - ፪፻፶፩ |
| | ፸፫ | የግራኝ አህመድ ወደ ባሌ መመለስ - የቃግማ ጦርነት የጀግናው የተክለ ሃይማኖት ፍጻሜ — በባሌ ግራኝ አህመድና ሽንቁር እንደተዋጉ (፲፭፻፳፪ ዓ. ም.) | ፪፻፶፮ - ፪፻፷፪ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፵፬ | የግዛት ስፋትና ያገዛዝ መላላት የፈጠረው የጦር ንት ጠንቅ ከዳተኞቹ ወናግ ካፐንና ልጁ ሲሙ (ሰምዖን) | [illegible] |
| | ፵፭ | የግራኝ አህመድ አዳዲስ መጣሪያ ይዞ ከሐረር ወደ ደዋሮ መምጣት — በአይፈርስ ጦርነት ዋዜማ በእጅ አዙር የራስ ደገልሃን በራስ እስላም ሰገድ መለወጥ — ለአይፈርስ ጦርነት የሁለቱ ባላጋራዎች ዝግጅት | [illegible] |
| | ፵፮ | አይፈርስ ላይ በራስ እስላም ሰገድና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገ ጦርነት (የካቲት ፲፭፻፳፫ ዓ.ም.) ከግራኝ ጋር ያሉት መድፎች የቤት ወደድ በድላይ ቅያሚ ጠላትን በመናቅ የሚደርስ የመሸነፍ ፍዳ | [illegible] |
| | ፵፯ | የዛሬ ጦርነት — የራስ እስላም ሰገድና የትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ሞት (ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) ግራኝ አህመድ ለዓፄ ልብነ ድንግል የጻፈው ደብዳቤ | [illegible] |
| | ፵፰ | ከአይፈርስና ከዛሬ ጦርነት በኋላ የግራኝ ጉዞ ወደ ዝቋላ — በዝቋላ ፥ በባደቄ ፥ በእንዶትና የቤተ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መዘረፍና መቃጠል (ሚያዝያ - ሐምሌ ፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) | [illegible] |
| | ፵፱ | የራስ ወሰን ሰገድ ከዳሞት መምጣት ለግራኝ አህመድ የጻፈለት ደብዳቤና የመጣለት መልስ (፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) | [illegible] |
| | ፶ | የራስ ወሰን ሰገድ ፕላን — የዝሆን ዱር ጦርነት — የዓምደ ሚካኤል አሟሟት (፲፭፻፳፫ ዓ.ም.) | [illegible] |
| | ፶፩ | የደብረ ሊባኖስ ገዳም መቃጠል — የመነኮሳቱ ከነበልባሉ ውስጥ መግባት (፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ሐምሌ ፳፱ ቀን) | [illegible] |
| | ፶፪ | ግራኝ ንጉሡን ከማባረር ሀብት ማባረር እንደ መረጠ — የራስ ወሰን ሰገድ ጦርነትና ሞት (ነሐሴ ፳ ቀን ፲፭፻፳፭ ዓ. ም.) | [illegible] |
| | ፶፫ | የራስ ወሰን ሰገድ የአሟሟት ዓይነት — የሕዝቡ በጅምላ መስለም | [illegible] |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፶፬ | በዚህ ዘመን የዓለም ሁኔታ ባጭሩ — ፖርቱጋል ለእርዳታ ፈጥኖ ያልደረሰበት ምክንያት | ፫፻፴፩ - ፫፻፴፰ |
| | ፶፭ | የአውራይ ኡስማን ወደ ግራኝ መግባት (መስከረም ፲፭፻፴፩ ዓ.ም.) — የምስሐለ ማርያም ቃጠሎ | ፫፻፴፰ - ፫፻፵፫ |
| | ፶፮ | በሸዋ ከተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ (፲፭፻፳፫ - ፳፬ ዓ. ም.) | ፫፻፵፬ - ፫፻፵፯ |
| | ፶፯ | በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የኑሮ ዕድል በየጊዜው መለዋወጥ | ፫፻፵፯ - ፫፻፶፪ |
| ፱ኛ | | ከሸዋ ወደ ቤተ አምሐራ መዛወር | |
| | ፶፰ | የዓፄ ልብነ ድንግል ከወጅ ወደ ቤተ አምሐራ (ሐገ) መዛወር (፲፭፻፳፫ ነሐሴ ፲፭፻፳፬ መስከረም)........................ | ፫፻፶፫ - ፫፻፶፯ |
| | ፶፱ | በማያት (ቤተ አምሐራ) የእዛዥ ደገልሃን ውጤት ያለው መከላከልና አዘንጊ ድል አድራጊነት (መስከረም - ጥቅምት ፲፭፻፳፬ ዓ.ም.) . | ፫፻፶፰ - ፫፻፷፫ |
| | ፷ | የዋሰል ጦርነት — የንጉሡ መሸነፍና መሸሽ (፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ጥቅምት ፳፪ ቀን) ....... | ፫፻፷፯ - ፫፻፸፫ |
| | ፷፩ | በቤተ አምሐራ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች ......................... | ፫፻፸፫ - ፫፻፹፩ |
| | ፷፪ | የአብያተ ክርስቲያናቱ አለቆች ወግና ማዕርጋቸው ......................... | ፫፻፹፩ - ፫፻፹፫ |
| | ፷፫ | መካነ ሥላሴ አትሮንስ ማርያም ደብረ ነጐድጓድ ኅዳር ፯ ቀን ፤ ቤተ ሰማያት ገነተ ጊዮርጊስ ኅዳር ፲፪ ቀን ፤ ደብረእግዚአብሔር ታኅሣሥ ፯ ቀን (፲፭፻፳፬ ዓ.ም.) እየተዘረፉ እንደተቃጠሉ | ፫፻፹፬ - ፫፻፹፱ |
| | ፷፬ | የደብረ እግዚአብሔር መቃጠልና በሐይቅ የመካነ እስጢፋኖስ መበዝበዝ (፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲ ቀን) — ከግራኝ ጋር ያሉት አረቦችና የውጭ አገር ሠራዊት - የዘመኑ ጥንቀላ . . | ፫፻፺ - ፫፻፺፱ |
| | ፷፭ | ስለ እምባ ግሼንና በላዩ ላይ ስላሉት መሳፍንት | ፬፻ - ፬፻፬ |


ISIC

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፵፮ | ገራድ አሀሙሽ ንጉሡን ፍሊጋ ሄዶ እፐቶ ሲመለስ እምባ ግሺንን እንደወጋ በእምባ ግሺን ጦርነት የግራኝ ጦር መሸነፍ የአሀሙሽ መማረክ፤ የገራድ ማታንና የአውራዩ ኢስማን ሞት (፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ኅዳር) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩፻፲ - ፩፻፲፩ |
| | ፵፯ | የግራኝ ወደ ሸዋ መመለስና ሞተ ተብሎ ስለመወራቱ — በደብረ ብርሃን የግራኝና የወዚር አዶሌ በታላቅ ሰልፍ መገኘት በዚያን ዘመን ወርቅ ስለመርከሱ (፲፰፻፵፩ - ፲፰፻፵፭ ዓ. ም.) . | ፩፻፲፪ - ፩፻፲፱ |
| | ፵፰ | የጀግናው የተክለ ጊዮርጊስና የራስ ነቢያት መካላከል (፲፰፻፵፩ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩፻፳ - ፩፻፳፫ |
| | ፵፱ | የተጉለት የደፋት የደዋሮና የመጀ የገዥላ ዙሪያ አገሮች ለግራኝ እየገቡ መስለም (፲፰፻፵፩ - ፲፰፻፵፭ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩፻፳፫ - ፩፻፳፮ |
| | ፶ | የማያ ሕዝብ ከነ፬፻፶ው ወደ ግራኝ መግባትና መስለም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩፻፳፯ - ፩፻፳፱ |
| | ፶፩ | የሐድያው ባላባት ለግራኝ አሀመድ መግባት . . | ፩፻፳፱ - ፩፻፴፩ |
| | ፶፪ | የዘላሀ (ባሊ) ጦርነት (፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ነሐሴ) የጆግናው የአዝማች አዳሉ ውጊያና አሟሟት | ፩፻፴፩ - ፩፻፵ |
| | ፶፫ | ስለ አዝማች አዳሉ (አዳል ሰገድ) . . . . . . . . | ፩፻፵ - ፩፻፵፩ |
| | ፶፬ | አዝማች አዳሉ የተዋጋለት በተማረኩት ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ፍርድ — የአዝማች አዳሉ ባለቤት መጥፎ ዕድል . . . . . . . . . . . | ፩፻፵፩ - ፩፻፵፫ |
| | ፶፭ | የጋንዝና የወረባ ለግራኝ አሀመድ መግባት (፲፰፻፵፭ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፩፻፵፫ - ፩፻፶፩ |
| | ፶፮ | ግራኝ ወደ ሰሜን ፀኛ ከመዝመቱ በፊት የደቡብ ግዛቱን እያስፋፋ እንደያዘ . . . . . . . . . | ፩፻፶፩ - ፩፻፶፪ |
| | ፶፯ | በግድም ተክለ ሃይማኖት ያደረገው መከላከል | ፩፻፶፪ - ፩፻፶፫ |
| | ፶፰ | የአምባ ግሺን ተራራ ፀኛ መከበብና የክርስቲያኖቹ መመከት (፲፰፻፵፭ ዓ. ም. ግንቦት - ሰኔ) | ፩፻፶፫ - ፩፻፶፯ |
| | ፶፱ | በላስታ (ወርወር) የላሊበላ ቤተ ክርስቲያን መበዝበዝ (፲፰፻፵፭ ዓ. ም. ሰኔ - ሐምሌ) . . . . . . | ፩፻፶፯ - ፩፻፷ |
| | ፷ | የግራኝ አሀመድ ጉዞ ወደ ትግሬ — የዘሐርቡይ መሐመድ ሞት (፲፰፻፵፮ ዓ. ም. መስከረም) . . | ፩፻፷፩ - ፩፻፷፮ |

| ክፍል ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፹፩ | የእንደርታ የተምቤንና የአጋሜ ጦርነት (፲፭፻ ፳፮ ዓ. ም. መስከረም - ጥቅምት) አህመድ አን ነጋሽ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ምክንያትና መቃብሩ .......... ............ | ፻፸፱ - ፻፹፪ |
| ፹፪ | የአክሱም ከተማና ሐውልት — የበለው ነገድ ከግራኝ ጋር መተባበር — በአምባ ሠነይት አጠገብ በአርአዳ ግራኝ የፈጀው ሕዝብ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ኅዳር - ታኅሣሥ) .............. | ፻፹፪ - ፻፹፯ |
| ፹፫ | የአክሱም ጽዮን ጽላተ ሙሴ — መክትር የመ ዘጋ ባላባት ከግራኝ ጋር ስለመደረቡ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ጥር - የካቲት) .............. | ፻፹፯ - ፻፺፩ |
| ፹፬ | ግራኝ አህመድ ንጉሡን ለመማረክ ከመዘጋ በጸ ለምትና በደምቢያ አድርጎ ወደ ጐጃም እንደ ገሠገሠ — ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ዓባይ ዳር ሊማረኩ ሲሉ ለጥቂት በ[illegible] አምልጠው እንደ ሄዱ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. የካቲት ፳፪ ቀን) — ከግዕ ዝና ከአማርኛ የተቀየጠ ቋንቋ ........... | ፻፺፩ - ፻፺፫ |
| ፹፭ | የዓቃቤ ሰዓትና የእጨጌ ልዩነት - ስለ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስና ስለ ቀኝ ጌታ ወሰንጌ ሞት | ፻፺፫ - ፻፺፯ |
| ፹፮ | የወዚር አዶሌ በሠራዬ ሹም በተሰፋ ልዑል እጅ መሞት (፲፭፻፳፯ ሐምሌ) .............. | ፻፺፯ - ፪፻፮ |
| ፹፯ | የኢትዮጵያ ንጉሥ ያፄ ልብነ ድንግል መልክ ተኛ አልቫሬጽ በፖርቱጋል ንጉሥ መልክተኛ በማርቲኖ አማካይነት ደብዳቤውንና ገጸ በረከ ቱን ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ እንዳ ቀረበ (እንደ አው ቀ. ፲፭፻፴፪ ግንቦት ፳፰ ቀን) | ፪፻፮ - ፪፻፲፱ |
| ፹፰ | ባፄ ልብነ ድንግል ዙሪያ ያሉት ፈረንጆች ከመካከላቸው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ወደ ሮምና ወደ ሊስቦን እንደተላከ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም.) . . . . | ፪፻፲፱ - ፪፻፳፫ |
| ፹፱ | በትግሬ ረሃብና በሽታ ተነሥቶ እስላሞችን እን ደፈጀ (፲፭፻፳፯ ዓ.ም.) — በትግሬና በሐማሴን የተደረገው ሹም ሽር ................... | ፪፻፳፫ - ፪፻፳፮ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፶ | የዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ መዳከም በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች የሰም አበራር ልዩነት በግ ድም ያፄ ልብነ ድንግልና የኢማም ሰምዮን መኰ ንን (፲፭፻፳፯ ኅዳር ፲፫ ቀን የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት . . . . . . . . . . . . | ፲፻፳፯ - ፲፻፴ |
| | ፶፩ | ግራኝ አህመድ ከትግሬ ወደ በጌምድር ሲዘምት ከሻውልና ከአዝማች ዮሐንስ ጋር ያደረገው ጦር ነት (፲፭፻፳፯ ሚያዝያ) . . . . . . . . . . | ፲፻፴፩ - ፲፻፴፫ |
| | ፶፪ | የአይሁድ የክርስቲያንና የእስላም ልዩነቱና ግንኙነቱ ስለፈላሾች . . . . . . . . . . | ፲፻፴፬ - ፲፻፵፪ |
| | ፶፫ | የባሕር አምባ ክርስቲያኖችና የፈላሾች የቆየ ጠብ የስሜንና የወገራ ለግራኝ መገዛት (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ሚያዝያ . . . ነሐሴ) | ፲፻፵፫ - ፲፻፵፭ |
| | ፶፬ | ግራኝ አህመድ በየአውራጃው ሹማምንቱን በስ መት ከደለደለ ISIC©ላ ደምቢያን የራሱ መቀመጫ እንድትሆን መርጦ እንደተቀመጠባት . . . . | ፲፻፵፮ - ፲፻፶፪ |
| | ፶፭ | በጣና ሐይቅ ስላሉት ደሴቶችና በየደሴቱ ላይ ስላሉት ገዳማት ስለ ደብረ ገሊላ መበዝበዝ (፲፭፻፳፱ ዓ.ም.) ስለ ዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ መቋረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፶፫ - ፲፻፶፱ |
| | ፶፮ | የግራኝ አህመድና የበላይ ሹንቅሎች ጦርነት የግራኝ በሥልጣኑ መደላደል . . . . . . . . | ፲፻፷ - ፲፻፷፩ |
| | ፶፯ | ግራኝ አህመድ ከዓፄ ልብነ ድንግል ልጅ ጋር ለመጋባት ጠይቆ ንጉሡ እንዳልተቀበሉት (፲፭፻፴፩ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፷፪ - ፲፻፷፰ |
| | ፶፰ | የጦርነቱና የመከራው ጽናት የአቤቶ ፊቅጦር ሞት ሚያዝያ ፲፱ የአቤቶ ሚናስ መማረክ ግንቦት ፳፫ ቀን(፲፭፻፴፩ ዓ.ም.) . . . . . . . . | ፲፻፸ - ፲፻፸፯ |
| | ፶፱ | የኢማም ኢመርና ያፄ ልብነ ድንግል የቸው ጦርነት (፲፭፻፴፩ ሰኔ ፲፯) የኢመር ባንድ ተራ ሰው እጅ ተወግቶ መሞት (፲፭፻፴፪ ዓ. ም.) . | ፲፻፸፰ - ፲፻፸፱ |
| | ፷ | የማሸን አምባ መበዝበዝ (፲፭፻፴፪ ዓ. ም. የካቲት ፫ ቀን) ንግሥታቱ ያደሰቡት ሀብት መልሰ አገሬ ቱን አስጠቃ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፹ - ፲፻፹፯ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፻፩ | በኢትዮጵያ የደረሱት ጦርነቶች — የግራኝ አህመድ ጽኑ ተዋጊነት — ያፄ ልብነ ድንግል ዕረፍት (፲፭፻፴፪ ዓ. ም. መስከረም ፭ ቀን) . . . | ፭፻፸፯ - ፭፻፹፫ |
| ፭ኛ | | **ያፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት** | |
| | ፻፪ | ያፄ ገላውዴዎስ ዕድገትና ንግሥ (፲፭፻፴፪ - ፲፭፻፴፫ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፭፻፹፬ - ፭፻፹፯ |
| | ፻፫ | ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡበት በመዠመሪያው ዓመት ከግራኝ አህመድ የጦር አለቆች ከወዚር አሳ ከገራድ ኡስማንና ከነድልበ ኢየሱስ ጋር ያደረጉት ጦርነት (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲፩ ቀን) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፭፻፹፯ - ፭፻፺፩ |
| | ፻፬ | ዓፄ ገላውዴዎስ በሰሜን ከገራድ ኡስማን ከወዚር ሙጃሂድና ከናስር ዲን ጋር እንደተዋጉ (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. የካቲት - ሚያዝያ) . . . . . . . . | ፭፻፺፩ - ፭፻፺፫ |
| | ፻፭ | የሶሊማን ፓሻ ጉዞ ወደ ዲው ወደብ (ሕንድ) — | ፭፻፺፬ - ፭፻፺፮ |
| | ፻፮ | በዲው ወደብ ላይ የሶሊማን ፓሻ ተሸንፎ መመለስ — ሲሄድና ሲመለስ በየመንገዱ በዓረቦች መሳፍንት ላይ የሠራው ግፍና የራሱ ፍጻሜ ። | ፭፻፺፯ - ፮፻፪ |
| | ፻፯ | የእስጢፋኖስ ደጋማ ከጐአ ወደ ስዌዝ መዝመት (፲፭፻፴፫ የካቲት - ግንቦት) . . . . . . . . | ፮፻፪ - ፮፻፯ |
| | ፻፰ | የአርኪቆ ወደብ መመታት — የኑር በጥይት ተመትቶ መሞትና ጭንቅላቱ ወደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል መላክ (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ግንቦት - ሰኔ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፮፻፯ - ፮፻፲፩ |
| | ፻፱ | የክርስቶፎሮስ ደጋማ መሾም . . . . . . . . . . . | ፮፻፲፪ - ፮፻፲፭ |
| | ፻፲ | ከምጥዋ እስከ ደባርዋ የፖርቱጋሎቹ ጉዞ (፲፭፻፴፫ ሐምሌ ፲፭ - ፳፭ ቀን) . . . . . . . . . . . . | ፮፻፲፭ - ፮፻፲፮ |
| | ፻፲፩ | በታሪክ ነገሥት በኩል ያለው የፖርቱጋሎቹ አመጣጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፮፻፲፯ - ፮፻፳፩ |
| | ፻፲፪ | የግራኝ አህመድ ቸልታ — ስለ ደብረ ዳሞ ተራራና ስለ አቡነ አረጋዊ ገዳም — የንግሥት ሰብለ ወንጌልና የክርስቶፎሮስ በደባርዋ መገናኘት (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ሐምሌ) . . . . . . . . . . | ፮፻፳፩ - ፮፻፳፱ |


ISIC

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፻፲፫ | የንግሥት ሰብለ ወንጌልና የፖርቱጋሎች ጉዞ ያፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤና የትዱስ ፊቅጦር ትንቢት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፳፱ - ፲፻፴፫ |
| | ፻፲፬ | ክርስቶፎሮስ ደጋማ በአምባ ሠናይት ከግራኝ ጋር ተዋግቶ እንደ አሸነፈ (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. የካቲት ወር) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፴፫ - ፲፻፴፯ |
| | ፻፲፭ | ዓፄ ገላውዴዎስ ከስሜን ወደ ሸዋ ሄደው ከግራኝ አህመድ ልጅ ከነስረዲን (ናስር አድ - ዲን) ጋር እንደተዋጉ በሸዋ የድል ሥራ መሥራታቸው (፲፭፻፴፬ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፴፰ - ፲፻፵፫ |
| | ፻፲፮ | ግራኝ አህመድና ክርስቶፎሮስ ደጋማ በመካከላቸው የተመላለሱት ደብዳቤ | ፲፻፵፫ - ፲፻፵፮ |
| | ፻፲፯ | ፖርቱጋሎችና ኢትዮጵያውያን ከግራኝ ጋር በሰሐርት (እንደርታ) ተዋግተው እንዳሸነፉ (፲፭፻፴፬ ዓ. ም. መጋቢት ፳፬ ቀን) . . . . . | ፲፻፵፯ - ፲፻፶፫ |
| | ፻፲፰ | ክርስቶፎሮስ ደጋማ ግራኝን እየባረረ ለመውጋት ሳይሳካለት እንደቀረና ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ወደ አሸንጌ ሐይቅ እንደሄዱ (፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ሚያዝያ - ነሐሴ) . . . . . . . . . . | ፲፻፶፫ - ፲፻፶፮ |
| | ፻፲፱ | የአቢቶ ሚናስ ወደ ዘቢድ ባሻ መላኩ ግራኝ አህመድ አዳዲስ የጦር መሣሪያና የቱርክ ወታደር ከዓረብ አገር እንዳስመጣ (፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ሚያዝያ - ነሐሴ) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፶፯ - ፲፻፷፬ |
| | ፻፳ | የክርስቶፎሮስ ደጋማ ስሜን ደርሶ መመለስ ከአሸናፊ ጋር የመደረብ ግዴታ . . . . . . . . . . . | ፲፻፷፬ - ፲፻፷፮ |
| | ፻፳፩ | በወፍላ የግራኝ አህመድና የፖርቱጋሎች መዋጋትና የፖርቱጋሎች መሸነፍ፣ የክርስቶፎሮስ ደጋማ ከፉኛ መቁሰል (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም ፫ ቀን) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፷፯ - ፲፻፸፫ |
| | ፻፳፪ | የክርስቶፎሮስ ደጋማ መማረክና መገደል (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም) . . . . . . . . . . | ፲፻፸፫ - ፲፻፹ |
| | ፻፳፫ | የተረፉት ፖርቱጋሎችና ንግሥት ሰብለ ወንጌል ካፄ ገላውዴዎስ ጋር በስሜን እንደተገናኙ (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ጥቅምት) . . . . . . . . . . | ፲፻፹ - ፲፻፹፩ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፻፷፬ | በግራኝ አህመድ ዘንድ ፪ኛው የጥንቃቄ መጉደል — የአሪያስ ዲያዝ በፖርቱጋሎቹ ላይ መሾም — በወገራ የተደረገው ጦርነት (የካቲት ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . | ፮፻፹፭ - ፮፻፹፱ |
| | ፻፷፭ | የጦር ዝግጅት (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ጥቅምት — የካቲት)— ከግራኝ ጋር ለመዋጋት የተደረገ ጉዞ — — ጦርነቱና የግራኝ አህመድ ሞት (የካቲት ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . . . . . . | ፮፻፹፱ - ፮፻፺፱ |
| | ፻፷፮ | የግራኝ አህመድ አሟሟት በካስታንሆዞ አጻጻፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፮፻፺፱ - ፯፻፫ |
| | ፻፷፯ | የግራኝ አህመድ እውነተኛውና አሰተኛው ገዳይ — የሞተበት ቀንና ዓመት (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. የካቲት ፳፯ ቀን ረቡዕ በ፫ ሰዓት) . . . . . | ፯፻፫ - ፯፻፯ |
| | ፻፷፰ | የግራኝ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ችሎትና ጉድለት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፯፻፯ - ፯፻፲፪ |
| | ፻፷፱ | ከግራኝ አህመድ ሞት በ[illegible]ለተረፈው ጦርና ስለድል ወንበራ ሽሽት — በግራኝና በኢጣልያ ወረራ ዘመን ያገልጋዮችና የከዳተኞች ተመሳሳይ ዕድል . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፯፻፲፪ - ፯፻፲፯ |
| | ፻፸ | ከግራኝ ሞት በኋላ የንግሥት ሰብለ ወንጌልና ያፄ ገላውዴዎስ መገናኘትና የፋሲካን በዓል አብሮ መዋል — የክርስቶፎሮስ ዳጋማ የሙት ዓመት ተዝካር (፲፭፻፴፮ ዓ.ም. መስከረም) . . . | ፯፻፲፯ - ፯፻፲፱ |
| | ፻፸፩ | የሚጉኤል ደ. ካስታንሆዞና የሃምሳ ፖርቱጋሎች ወደ ሕንድ መመለስ (፲፭፻፴፮ ዓ. ም.) ዓፄ ገላውዴዎስ ስለካስታንሆዞ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፯፻፲፱ - ፯፻፳፬ |
| ፯ኛ | | **የሃይማኖት ክርክር** | |
| | ፻፸፪ | የክርስትና ሃይማኖት መመሥረት — በዓለም ላይ የድርጅቱ አከፋፈልና የጠቡ ምክንያቶች | ፯፻፳፭ - ፯፻፴ |
| | ፻፸፫ | በክርስትና እምነት የኢትዮጵያ ጉራ — የ፩ ባሕርዮችና የ፪ ባሕርዮች የቆየ ጠብና ክርክር | ፯፻፴፩ - ፯፻፴፯ |
| | ፻፸፬ | በወጅ ያፄ ገላውዴዎስና የወዚር አባስ ጦርነት (፲፭፻፴፮ ዓ. ም. ጥቅምት) . . . . . . . . . . . . | ፯፻፴፯ - ፯፻፵፪ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| | ፻፴፭ | በዮሐንስ ቤርሙዴዝና ባፄ ገላውዴዎስ መካከል የተቀሰቀሰው የመጀመሪያው ጠብ . . . . | ፲፻፹፪ - ፲፻፹፯ |
| | ፻፴፮ | ያፄ ገላውዴዎስና የቤርሙዴዝ ወደ ስምምነት መቅረብ — ዓፄ ገላውዴዎስ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለጳውሎስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ (፲፭፻፵፭ ዓ. ም. ኅዳር - ጥር ) . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፹፯ - ፲፻፺ |
| | ፻፴፯ | በቀሊምንጦስ ፯ኛ ምትክ የጳውሎስ ፫ኛ መሾም — የአውሮፓ ነገሥታት የርስ በርስ ጠብና በሉተር ቀስቃሽነት የተወጠነው የቤተ ክርስቲያን መሻሻል — ቤርሙዴዝ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንዲለወጥ ስለ መጠየቁ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፺ - ፲፻፺፯ |
| | ፻፴፰ | ፪ኛው የቤርሙዴዝ ጠብና ግዞቱ ስለ ግርቆስ — ስለ ቤርሙዴዝ ወደ አገሩ መመለስ (፲፭፻፴፯ ዓ. ም.) . ISIC . . . . . . . . . . . . | ፲፻፺፯ - ፲፻፻፩ |
| | ፻፴፱ | የዓፄ ገላውዴዎስ ኢትዮጵያ ከፖርቱጋልና ከቱርክ በቀል የዳነችባቸው ሰበቦች . . . . . . . . . | ፲፻፻፩ - ፲፻፲፩ |
| | ፻፵ | በሮማ ጳውሎስ ፫ኛ ሞተው ዩልዮስ ፫ኛ ስለ መሾማቸው — የኢየሱሳውያን ማኅበር መቋቋምና የሮድሪግ ጎንዛሎ በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (፲፭፻፵፫ ዓ. ም.) . . . . . . . . . . . | ፲፻፲፪ - ፲፻፲፯ |
| | ፻፵፩ | የአንድርያስ አቪዬዶ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (እ. አ. ቆ. ፲፭፻፵፯ ዓ.ም. መጋቢት) የገላውዴዎስ ንጉሣዊ ኃላፊነት በሁለት ተከራካሪዎች መካከል . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፲፰ - ፲፻፳፫ |
| | ፻፵፪ | ከአንድርያስ አቪዬዶ የቀረበው የሃይማኖትና የልማድ ክርክር — ከዓፄ ገላውዴዎስ የተሰጠው የመጨረሻ መልስ (፲፭፻፵፰ ዓ.ም. ሰኔ ወር) | ፲፻፳፬ - ፲፻፳፱ |
| | ፻፵፫ | ክርስትናን በስፍራው ለመመለስና ለመጠበቅ የተዘጋጁት መጻሕፍትና ተመልሰው የተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፴ - ፲፻፴፬ |
| | ፻፵፬ | የመሬትና የግዛት ጠብ በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካከል ኖሯል ? የፖርቱጋል በእስያ መንግሥት መጠቅለል . . . . . . . . . . . . . . | ፲፻፴፭ - ፲፻፴፰ |

| ክፍል | ምዕራፍ | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ፯ኛ | | **ያፄ ገላውዴዎስ ትግልና የሕይወታቸው ፍጻሜ ።** | |
| | ፻፵፭ | የአቡኑ ሚናስ በመሐመድ ተለውጦ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (፲፭፻፴፫ ዐ. ም.) ....... | ፯፻፹፱ - ፯፻፺፪ |
| | ፻፵፮ | አቡኑ ሚናስ ከምጥዋ ወደ ዐባይ መጥቶ ከእናቱ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ከተገናኙ በኋላ ከዓባይ ወደ ወጅ ሄዶ ከወንድሙ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር እንደተገናኙ (፲፭፻፵፩ ዓ. ም.) ... | ፯፻፺፪ - ፯፻፺፬ |
| | ፻፵፯ | የቱርኮች እንደገና ከምጥዋ መጥተው ደብረ ዳሞን ማፍረስና ኤርትራን መውረር — የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ክዳቱና ሞቱ ............ | ፯፻፺፬ - ፯፻፺፱ |
| | ፻፵፰ | ያፄ ገላውዴዎስ ከያዕቆብና ከሚናስ ጋር መስማማት ........................ | ፯፻፺፱ - ፰፻፩ |
| | ፻፵፱ | የጋሎች አመጣጥና የዘር ግንዳቸው ........ | ፰፻፩ - ፰፻፮ |
| | ፻፶ | ስለጋሎች ጦርነት በአባ ባሕርይና በቤርሙዴዝ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ማስረጃ ....... | ፰፻፯ - ፰፻፲፩ |
| | ፻፶፩ | የኑር ቤን ሙጃሂድ አነሣሥና ካፄ ገላውዴዎስ ጋር ለውጊያ መሰላለፍ (፲፭፻፶፩ ዓ.ም.) .... | ፰፻፲፩ - ፰፻፲፯ |
| | ፻፶፪ | ባፄ ገላውዴዎስና በአሚር ኑር መካከል የተደረገው ጦርነት — ያፄ ገላውዴዎስ ሞት (፲፭፻፶፩ መጋቢት ፳፫ ቀን) .............. | ፰፻፲፯ - ፰፻፳፪ |
| | ፻፶፫ | በጦርነቱ ላይ የሞቱት ያፄ ገላውዴዎስ ጭንቅላት ሐረር ሄዶ መሰቀል — በሐረር የተነሣው ታላቅ ረሃብ (፲፭፻፶፩ - ፶፫ ዓ. ም.) የደራሲው ኀዘን ........................ | ፰፻፳፫ - ፰፻፳፰ |
| | ፻፶፬ | የአሚር ኑርና የግራኝ አህመድ ተከታዮች ፍጻሜ ........................ | ፰፻፳፱ - ፰፻፴፫ |
| | ፻፶፭ | የሐረርጌ ከኢትዮጵያ ጋር እንደገና መዋሐድ (፲፰፻፸፱ ዓ. ም.) ................ | ፰፻፴፱ - ፰፻፵ |

## የስዕሎች ዝርዝር ማውጫ

ገጽ


አክሱማውያን በዘመናቸው ያሠሩዋቸው የመገበያያ ገንዘቦች . . . [illegible]
ዓፄ ይኩኖ አምላክ ለቤተ ክርስቲያናት የአላፎ ምድርን ጉልት
የሰጡበት ታሪካዊ ጽሑፍ . . . . . . . . . . [illegible]
የንጉሥ ታቱ የዘር ግንድ . . . . . . . . . . [illegible]
ባዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረው የብርዕ አጣጣል . . . . . . . . [illegible]
የእስጢፋኖስና የክርስቶፎሮስ አባት ስመጥሩው መርከበኛ ቫስኮ ደጋማ [illegible]
ፍራንቼስኮ ዳልማይዳ . . . . . . . . . . [illegible]
አልፎንስ ደ አልቡኬርክ . . . . . . . . . . [illegible]
ንጉሥ አማኑኤል በቤተ ክርስቲያን ሲጸልዩ . . . . . . . . [illegible]
የዓፄ ናዖድና የልጃቸው ያፄ ልብነ ድንግል በዲማ ጊዮርጊስ
የሚገኝ ሥዕል . . . . . . . . . . [illegible]
ዓፄ ልብነ ድንግል በዘመናቸው ያጻፉት የተአምረ ማርያም ሃንዱ
ምዕራፍ መጨረሻ የብርዑ አጣጣል . . . . . . . . [illegible]
ዓፄ ልብነ ድንግል ለሴት ልጆቻቸውና ለባለቤታቸው ርስተ ጉልት
የሰጡበት ጽሑፍ . . . . . . . . . . [illegible]
ዓፄ ዓምደ ጽዮን በኢየሩሳሌም ገዳም ISIC ላገኘው ለማርያም
መጽሐፈ ንጉሥት የሰጡበት ጽሑፍ . . . . . . . . [illegible]
ከዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታሪካዊ ድብዳቤ የመጀመሪያው ገጽ . . . . . . [illegible]
ሎሬ ሶአሬዝ ፫ኛው የሕንድ ገዥ . . . . . . . . [illegible]
ዲዩጐ ሎፔዝ . . . . . . . . . . [illegible]
የመልክተኞቹ መሪ ሮድሪጎ ደ ሊማ . . . . . . . . [illegible]
ዓፄ ልብነ ድንግል በ፳፫ ዓመት ዕድሜያቸው
የተሳሉት ሥዕል . . . . . . . . . . [illegible]
ሮድሪጎ ደ ሊማ በጉዞ ላይ . . . . . . . . በ፻[illegible] እና በ፻[illegible] መካከል
ዓፄ ልብነ ድንግል ደብዳቤ የጻፉለት ዮሐንስ ሳልሣዊ . . . . . . በ፻[illegible] እና በ፻[illegible] መካከል
የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን የአረብ ፋቂህን መጽሐፍ . . . . . . [illegible]
ያረብኛውን ታሪካዊ ጽሑፍ የሚያሳየው . . . . . . . . [illegible]
የግራኝ አህመድ የዘር ግንድ . . . . . . . . . . [illegible]
በቅርብ ጊዜ ከቱሉ ዲምቱ የተገኘው የጽላት ቅርጽ . . . . . . . . [illegible]
ግራኝ አህመድ ዓፄ ልብነ ድንግልንና ሠራዊታቸውን እየተከታተለ
የተዋጋባቸውን ሥፍራዎች የሚያመለክት ካርታ . . . . . . . . [illegible]
የዑመር ወላስማ የዘር ግንድ . . . . . . . . . . [illegible]
የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በአሁኑ ሁኔታ . . . . . . . . [illegible]
[illegible]

# የስዕሎች ዝርዝር ማውጫ


ገጽ

በብርብር ማርያም (ገሙጐፋ) ከሚገኝ ካንድ የብራና ወንጌል ዳር የተገኘ
ጽሑፍ ........................................ ፩፻፳፩
ዓፄ ልብነ ድንግል ለሳፍ ሰገድ ጉልት የሰጡበት ታሪካዊ
ሰነድ ......................... በገጽ ፩፻፳፪ እና ፩፻፳፫ መካከል
የሐድያ አውራጃ ሴት .................. በ፩፻፴ እና በ፩፻፴፩ መካከል
የላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ........................... ፩፻፵፩
የአክሱም ሐውልቶች ባጋማሽ የሚታዩት ....................... ፩፻፷፰
የዓፄ ልብነ ድንግል ዐጽም ያረፈበት የአቡነ አረጋዊ ገዳም ራቅ ብለው ሲያዩት
በ፩፻፷፰ እና በ፩፻፷፱ መካከል
የክርስቶፎሮስ ደጋማ ታላቅ ወንድም እስጢፋኖስ ደጋማ .......... ፪፻፬
ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሕይወቱን የሰዋው ክርስቶፎሮስ ደጋማና ፊርማው . . ፪፻፲፫
የደብረ ዳሞ ተራራ ራቅ ብለው ሲያዩት ..................... ፪፻፳፫
ደራሲው የደብረ ዳሞን ገዳም ለመጐብኘት በገመድ እየተሳበ ሲወጣ . . ፪፻፳፮
ደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ያለው የአቡነ አረጋዊ ገዳም በ፪፻ ፳፯ እና በ፪፻፳፰ መካከል
ክርስቶፎሮስ ደጋማ ከጭፍሮቹ ጋር ሆኖ እስላሞቹን ሲያባርር ...... ፪፻፵፱
ግራኝ አህመድ ካፄ ገላውዴዎስ ጋር ተዋግቶ የሞተበትን በደንቀዝ
የሚገኘውን የዘንተራን ሠፈር የሚያሳይ ካርታ ............... ፪፻ ፶
የግራኝ በር ቀበሌ ........................... ፪፻ ፶፩
ግራኝ ተመትቶ በቆሰለ ጊዜ ተበሳጭቶ በጕራዴ መታው የተባለው
ወይራ ወይቀኝ ያለው ......................... ፪፻ ፶፪
ግራኝ በጥይት ተመትቶ የወደቀበት የዘንተራ አቀበት ........... ፪፻ ፶፮
በደንቀዝ ውስጥ ዘንተራ በሚባለው ቀበሌ የሚገኘው የግራኝ መቃብር . . ፫፻፩
ደራሲው የግራኝን መቃብር ለመጐብኘት በሄደበት ቀን
ከሹማምንት ጋር ............................ ፫፻፪
ዓፄ ገላውዴዎስ ስለ ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ለፖርቱጋል ንጉሥ
ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ ...................... ፫፻፳፬
ዓፄ ገላውዴዎስ ስለዮሐንስ ቤርሙዴዝ ለሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት
የጻፉት ደብዳቤ .............................. ፫፻፵፱
ከሐረር አሚሮች አንዱ አህመድ ኢብን አቢባክር (አቡበከር) ....... ፫፻፸፪

ISIC

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ታሪክ በጽሑፍ ሰፍሮ ይነስ ይብዛ መደዳውን መገኘት የዠመረው ከአሥራ አራተኛው መቶ ዓመት ካፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን መንግሥት ዠምሮ ነው ። ከዚያ በፊት የአክሱም መንግሥት ኃይሉም ሥልጣኔውም የገነነ እንደነበረ ሲታወቅ በየዘመኑ ተጽፎ ወደ ጊዜያችን የተላለፈው በየምክንያቱ በጣም ከማነሱ የተነሣ ያብዛኞቹን ነገሥታት ዝርዝር ታሪካቸውን አናውቀውም ። ከአክሱም በምዕራብ በኩል የበጅያ ሕዝብ በሰሜን በኩል የስዕኔና የጸወንቴ ሕዝብ የሸፈተ ጊዜ ታላቁ ንጉሥ ዒዛና (አብርሃ) ራሱም ዘምቶ ወንድሙንም ልኮ በ፬ኛው መቶ ዓ.ም. ስለፈጸመው ጦርነት ፤ በሀገረ ናግራን በክርስቲያኖቹ ዕልቂት የተነሣ ዓፄ ካሌብ ወደ ዓረብ አገር በ፮ኛው ዘመን ዘምቶ ክርስቲያኖቹን ባጠቋቸው ይሁዲዎች ላይ የመለሰው የበቀል ውጊያ ፤ በ፲ኛው መቶ ዓመት ፈላሻዪቱ ዮዲት የአክሱምን መንግሥት አጥፍታ የራስዋን ገዥነት የመሠረተችበት ጦርነት ከገድል ፤ ከድርሳንና ከአፈ ታሪክ ውጭ ተረትና መላ ባልተደባለቀበት መንገድ የምናገኘው ሐቀኛ የታሪክ ጽሑፍ መጠኑ ትንሽ ነው ። ሐቀኛ ታሪክ የምንለውም ፩ኛ ፤ እነፕሮፌሰር ኢኖ ሊትማን በአክሱምና በአካባቢው በዩሐ ፤ በማጠራ በከስከሴ በሌሎቹም የታሪክ ቦታዎች ካጠራቀሙት የሐውልትና የገንዘብ ጽሑፎች ላይ የተገኘው ፤ ፪ኛ ፤ ባንዳንድ በተበታተኑ የብራና ጽሑፎች ላይ ሠፍሮ የሚገኘው ታሪካዊ ማስረጃ ነው ። ካፄ ዓምደ ጽዮን ወዲህ እስከ ፲፱ኛው መቶ ዓመት ድረስ ያለው ጽሑፍም አብዛኛው የጦርነት አጫጭር ታሪክ እየሆነ በዛሬ ዘመን አስተሳሰብ የስነ ጽሑፍ ደረጃ አንሶ ይታያል ።

የፈላሻዋ የዮዲት ግዛት የቆየው አርባ ዓመት ነው የሚለውን መሠረት ያደረግን እንደሆነ በዘመን ርዝማኔ አሥራ አምስት ዓመት ከቆየው ከግራኝ አህመድ የወረራ አገዛዝ የርሷ ስለሚረዝም በዚያው መጠን በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ የመከራው ጊዜ በርክቶ ይሆናል ብሎ ለማሰብ መንገድ ይሰጣል ። ነገር ግን ዮዲት ከተነሣችበት ጊዜ ዠምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የግራኝ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ወረራ ያመጣውን ያህል የጦርነትና የእልቂት መከራ በኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ ምን ጊዜም ደርሶ አያውቅም ። የኢጣልያ የአምስቱ ዓመታት ወረራና ሥቃይ ፤ የየካቲት ፲፪ ቀን ዕልቂት ተጨምሮ የ፲፭ቱን ዓመታት የግራኝን ወረራና ዕልቂት አይተካከለውም ።

ዮዲትን አክሱም በተዳከመበት ሰዓት ለመነሣትና በአክሱሞች ክርስቲያኖች ላይ ያስጨከናት ዝርዝር ጉዳዩን በሰነድ መልክ ባናገኘውም በኋለኛው ባፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን እንደሆነው ምናልባት በአክሱም ክርስቲያኖቹ ነገሥታትና መኳንንት በገናንነት በነበሩበት ሰዓት ክርስትናን ለማስፋፋት ባላቸው ምኞት የተነሣ ፈላሾቹን ወደ ክርስትና ለማምጣት በፈጸሙት የጭካኔ አስገዳጅነት ምክንያት ይሆናል ። አሁንም የግራኝ አህመድን የጭከና ወረራ ከመመልከት በፊት በዋዜ

ማው በነበረው የሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት ጊዜ ውስጥ በክርስቲያኖቹ ነገሥታትና በእስላሞቹ በወላስማ ተከታዮች መካከል በየጊዜው የተፈጸመውን የጦርነት ትግል ስናነብ የግራኝንና የተከታዮቹን የጭካኔያቸውን ሰበብ በግልጥ እንረዳለን ።

ከነቢዩ መሐመድ ስብከት ወዲህ (፯ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት) ከግራኝ አህመድ አነሣሥ (፲፮ኛው መቶ ዓ.ም.) በፊት በሚገኘው የዘጠኝ መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከቀይ ባሕር ማዶ የመጡ የልዩ ልዩ ነገድ ዓረቦች ሃይማኖት ለማስፋፋት ፥ የነርሱን የንግድ ሸቀጥ በኢትዮጵያ ለማስገባት ፥ ከነርሱ የማይገኘውን ከዚህ ለመላክ ወይም የተሻለ መሬትና ኑሮ ፍለጋ ፥ ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ በበረከቱ መጠን በስብከትም በጋብቻም ከነርሱ የተገናኘው ያገር ተወላጅ በተለይ ክርስትናን ያልተቀበለው የሱማሌው ፥ የደንከሉ ፥ የጥልጣሉ ፥ የአዳሉ ፥ የኢሳው ተወላጅ ከነርሱ ተምሮ እስልምናን የተቀበለው መበርከት ዠመረ ። በኢትዮጵያ ያቡብ በሐድያ በባሌ እየገቡ እንደነ ሼክ ሁሴን ያሉት የሃይማኖት መሪዎች ተመሠረቱ ። በዚሁ ዓይነት ከዓረብ አገር መጥቶ ለአዳል አገር በማያርቀው በይፋት የተመሠረተው ኡመር ወላስማ በቀን ብዛት ከመጣተኝነት ወደ ባላባትነት ከዚያም ወደ መስፍንነት ዞሮ በቅድሚያ አመሉንና ተገዥነቱን ስለአሳመረ በንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድ የይፋት መስፍን አንዳንድ ጊዜም የአዳል ንጉሥ እየተባለ በመጡት ዓረቦችና እስላምነክ በሆኑት እላይ በጠቀስናቸው የይፋትና የአዳል አገሮች ላይ ገዥነቱን ተከለ ።

ኡመር ወላስማ በይፋት ገብቶ የተተከለበት ጊዜ ሲታሰብ ዓፄ ይኩኖ አምላክና ዓፄ አግብአ ጽዮን ከነበሩበት ጊዜ (፲፪፻፸፱ - ፲፪፻፺፱ ዓ. ም.) ጋር ይገናኛል ። ስለዚህ ኡመር ወላስማን በአዳልና በይፋት ላይ በፈቃዳቸው የሾሙ እነዚሁ የኢትዮጵያ ነገሥታት ናቸው ። በሚቀጥለው ጊዜ የኡመር ወላስማ ተከታዮች ሳይመቻቸው ለክርስቲያኖቹ ለኢትዮጵያ ነገሥታት እየገበሩ ሲመቻቸው ነፃ ለመሆንነት እስከ ግራኝ መነሣት ድረስ እንደቀጠለ ነበር ። በዚህም በየጊዜው ብዙ ደም መፋሰስና መዘራረፍ በሁለቱም ወገን ተፈጽሟል ።

በታሪክ እንደምናስታውሰው ራሱ ወላስማ የሸፈተበት ጊዜ ጽሑፍ አይገኝም ። ነገር ግን የወላስማ ልጆች ደራደር ፥ ሐቀ ዲን ፥ ነስረዲን ፥ የልጁ ልጅ ጋማል ዲን ፥ የልጅ ልጁ ልጅ ሰብረዲን (ሳብር አድ ዲን) ከአፄ ዓምደ ጽዮን ጋር ፥ የሰብረ ዲን ልጅ አሊ ከዓፄ ንዋየ ክርስቶስ (ሰይፈ አርእድ) ጋር ፥ የአሊ የልጅ ልጅ ሐቀ ዲን (ሐቅ አድ ዲን) ካፄ ንዋየ ማርያም (ውድም አስፈሬ) ጋር ፥ የሐቀ ዲን ወንድም መሐመድ አቡል በረከት ሰዓድ ዲን ካፄ ዳዊት ጋር ፥ ልጁ በድላይ ሺሃብ አህመድ (ታሪክ ነገሥቱ አርዌ በድላይ የሚለው) ካፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር ፥ የርሱ ልጅ ሰለይማን መሐመድ ካፄ በዕደ ማርያም ጋር ፥ የርሱ የወንድም ልጅ ሻምስ አድ ዲን መሐመድ ካፄ እስክንድር ጋር ፥ መሐመድ ኢብን አዝሐርዲን ካፄ ናዖድ ጋር ሲዋጉ ኖረዋል ። ይኸም ስለሆነ ከኡመር ወላስማ ዠምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል አባት እስከ ዓፄ ናዖድ ድረስ ያሉት መደዳውን ሲዋጉ ኖረዋል ማለት አይደለም ። ኡመር ወላስማን የይፋት ገዥ እንዲሆን የሾመው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነ

ሥት (ይኩኖ አምላክ ወይም ልጁ አግብአ ጽዮን) መሆኑን ብዙ ጊዜም የኡመር
ወላስማ ተወላጆች ለኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት እየገበሩ መኖራቸውን አል ማክ
ሪዚ በታሪክ መጽሐፉ ያረጋግጣል ። እነዚህ አልፎ አልፎ የሚሸፍቱትም እንደ
ግራኝ አህመድ የኢትዮጵያን ነገሥታት አሸንፈው አገሪቱንም ወርረው አያው
ቁም ። በዚህ ፈንታ በተነሡ ቍጥር እየተሸነፉ ሲገብሩ ኖረዋል ። አንዳንድ ጊዜ
ባንዳንድ ውጊያ ላይ ቢቀናቸውም መደምደሚያውን ከመሸነፍና ከመገበር አል
ፈው አያውቁም ። ብዙ ጊዜም አንደኛው ሲሸፍት ወንድሙ ለኢትዮጵያ ንጉሥ
ታማኝ ሆኖ እየገበረ ያባቱን ግዛት እየተሾመ በሰላም መኖሩ በየታሪኩ ውስጥ
ጣልቃ ገብቶ ይታያል ።

በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ግድም በአቡበከር ባራካት (የአህመድ በድላይ የወንድም
የልጅ ልጅ) ጊዜ መደበኛ ሥፍራው ከይፋት ወደ አዳል (ዳካር) ተዛውሮ በዳካር
ከትሞ ይኖር የነበረው የወላስማ ቤት ወደ ሐረርጌ ተዛወረ ። ይህ ዘመን (፲፭፻፲፱
ዓ. ም.) የግራኝ የወጣትነቱ ዘመን መሆኑ ነው ። በገዥዎቹና በተገዥዎቹ መካ
ከል ያለው ጠብና ጦርነት ሲጠፋ ሲለማ የኢትዮጵያ ነገሥታትም የሸፈተውን
ሲሽሩ የታመነውን ወንድሙን ሲሾሙ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት
ደረሱ ።

ISIC

ወላስሞቹ በገዥዎቻቸው በኢትዮጵያ ነገሥታት ላይ ሸፍተው በተነሡ
ቍጥር እርዳታ የሚያገኙት ከማዶ ከሃይማኖት ወገኖቻቸው ከዓረብና ከግብፅ
ነው ። ለውጊያ የሚከተላቸውም ሕዝብ እላይ የጠቀስነው ቀደም ብሎ ባለው
ዘመን ወደእስላምሃይማኖት ያስገቡትና በእምቻ በጋብቻ አብሮ በመኖር ያቀረቡት
የደንከል የአዳልና የኢሳ የሱማሌ አንዳንድ ጊዜም ከወዲህ ያለው የሐድያ የባሌ
የደዋሮ ተወላጅ ነው ። ይሁን እንጂ ከወዲህም ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ታማኝ
ሆኖ እነሱን የሚወጋ የአዳልና የኢሳ ሕዝብ አንዳንድ ጊዜም የዓረብ ተወላጅ ላይ
ቀር መኖሩን ወደ ዋናው ታሪክ ስንገባ እንረዳለን ። የግራኝ አህመድ አሸናፊነት
የንጉሡ ተሸናፊነት ተስፋ አስቆርጦት በመጨረሻ እስኪከዳ ድረስ ከንጉሡ ጋር
ሆኖ በብዙ ቦታ የግራኝን ጦር ሲወጋ የኖረውን አውራይ ኡስማን ቤን ዳር አሊን
ለምሳሌ ያህል ማስታወስ ይቻላል ። እንደዚሁም ከወዲህ ተበደልሁ የሚል የክርስ
ቲያን መኰንን ከንጉሡ ሸፍቶ ወደነርሱ የገባና መሣሪያ የሆነ ይገኛል ። ለምሳሌ
ባዔ ናዖድ ጊዜ ሹመቱ ለሌላ ስለተሰጠበት ንጉሡን ከድቶ ለመሐመድ ኢብን አዝ
ሐር ያደረው የራስ ወሰን ሰገድ ወንድም ወናግ ዣን የሚባለው ይገኛል ።

ክርስቲያኖቹና እስላሞቹ ከሥር ከመሠረቱ ከሴምና ከካም ከኩሽ የፈለቁ
በዘር በቋንቋና በልማድ የተሣሰሩ ወገኖች እንደ መሆናቸው መጠን በመጋባት
በመፋቀር ፋንታ በዚያን ጊዜ በሃይማኖትና የሃይማኖት ሕግ በሰጠው ውሳኔ ፤
በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ልማድ ምክንያት ሁለቱ ወገኖች ስለተለያዩ በሰላም አብሮ
የመኖር ዘዴ መፍጠር አቅቷቸው ነበር ። በዚህ ፈንታ የነዚህ ትምክህት ክርስቶስ ፤
[illegible] ወንጌል ሲሆን ፤ የነዚያ

ማው በነበረው የሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት ጊዜ ውስጥ በክርስቲያኖቹ ነገሥታ ትና በእስላሞቹ በወላስማ ተከታዮች መካከል በየጊዜው የተፈጸመውን የጦርነት ትግል ስናነብ የግራኝንና የተከታዮቹን የጭካኔያቸውን ስበብ በግልጥ እንረዳለን ።

ከነቢዩ መሐመድ ስብከት ወዲህ (፯ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት) ከግራኝ አህ መድ አነሣሥ (፲፮ኛው መቶ ዓ.ም.) በፊት በሚገኘው የዘጠኝ መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከቀይ ባሕር ማዶ የመጡ የልዩ ልዩ ነገድ ዓረቦች ሃይማኖት ለማስፋፋት ፤ የነርሱን የንግድ ሸቀጥ በኢትዮጵያ ለማስገባት ፤ ከነርሱ የማይገኘውን ከዚህ ለመ ላክ ወይም የተሻለ መሬትና ኑሮ ፍለጋ ፤ ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ በበረከቱ መጠን በስ ብከትም በጋብቻም ከነርሱ የተገናኘው ያገር ተወላጅ በተለይ ክርስትናን ያልተቀ በለው የሱማሌው ፤ የደንከሉ ፤ የጥልማሉ ፤ የአዳሉ ፤ የኢሳው ተወላጅ ከነርሱ ተምሮ እስልምናን የተቀበለው መበርከት ዠመረ ። በኢትዮጵያ ደቡብ በሐድያ በባሌ እየገቡ እንደነ ሼክ ሁሴን ያሉት የሃይማኖት መሪዎች ተመሠረቱ ። በዚሁ ዓይነት ከዓረብ አገር መጥቶ ለአዳል አገር በማይርቀው በይፋት የተመሠረተው ኡመር ወላስማ በቀን ብዛት ከመጣተኝነት ወደ ባላባትነት ከዚያም ወደ መስፍን ነት ዞሮ በቅድሚያ እመሉንና ተገዥነቱን ስለአሳመረ በንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድ የይ ፋት መስፍን አንዳንድ ጊዜም የአዳል ንጉሥ እየተባለ በመጡት ዓረቦችና እስላም ነክ በሆኑት እላይ በጠቀስናቸው የይፋትና የአዳል አገሮች ላይ ገዥነቱን ተከለ ።

ኡመር ወላስማ በይፋት ገብቶ የተተከለበት ጊዜ ሲታሰብ ዓፄ ይኩኖ አምላ ክና ዓፄ አግብአ ጽዮን ከነበሩበት ጊዜ (፲፪፻፷፪ - ፲፪፻፹፮ ዓ. ም.) ጋር ይገናኛል ። ስለዚህ ኡመር ወላስማን በአዳልና በይፋት ላይ በፈቀዳቸው የሾሙ እነዚሁ የኢት ዮጵያ ነገሥታት ናቸው ። በሚቀጥለው ጊዜ የኡመር ወላስማ ተከታዮች ሳይመቻ ቸው ለክርስቲያኖቹ ለኢትዮጵያ ነገሥታት እየገበሩ ሲመቻቸው ነፃ ለመሆን ወይም የክርስቲያኑን መንግሥት ለመገልበጥ ከክርስቲያኖቹ ጋር ያደረጉት ጦር ነት እስከ ግራኝ መነሣት ድረስ እንደቀጠለ ነበር ። በዚህም በየጊዜው ብዙ ደም መፋሰስና መዘራረፍ በሁለቱም ወገን ተፈጽሟል ።

በታሪክ እንደምናስታውሰው ራሱ ወላስማ የሸፈተበት ጊዜ በነማክሪዚ ጽሑፍ አይገኝም ። ነገር ግን የወላስማ ልጆች ደራደር ፣ ሐቀ ዲን ፣ ነስረዲን ፤ የልጁ ልጅ ጋማል ዲን ፤ የልጅ ልጁ ልጅ ሰብረዲን (ሳብር አድ ዲን) ከአፄ ዓምደ ጽዮን ጋር ፣ የሰብረ ዲን ልጅ አሊ ከዓፄ ንዋየ ክርስቶስ (ሰይፈ አርእድ) ጋር ፣ የአሊ የልጅ ልጅ ሐቀ ዲን (ሐቅ አድ ዲን) ካፄ ንዋየ ማርያም (ውድም አስፈሬ) ጋር ፤ የሐቀ ዲን ወንድም መሐመድ አቡል በረከት ሰዓድ ዲን ካፄ ዳዊት ጋር ፣ ልጁ በድ ላይ ሺሃብ አህመድ (ታሪክ ነገሥቱ አርዌ በድላይ የሚለው) ካፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር፤ የርሱ ልጅ ሶለይማን መሐመድ ካፄ በዕደ ማርያም ጋር ፤ የርሱ የወንድም ልጅ ሻምስ አድ ዲን መሐመድ ካፄ እስክንድር ጋር ፤ መሐመድ ኢብን አዝሐርዲን ካፄ ናዖድ ጋር ሲዋጉ ኖረዋል ። ይኸም ስለሆነ ከኡመር ወላስማ ዠምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድን ግል አባት እስከ ዓፄ ናዖድ ድረስ ያሉት መደዳውን ሲዋጉ ኖረዋል ማለት አይደ ለም ። ኡመር ወላስማን የይፋት ገዥ እንዲሆን የሾመው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገ

ISLC

ሥት (ይኵኖ አምላክ ወይም ልጁ አግብአ ጽዮን) መሆኑን ብዙ ጊዜም የኡመር
ወላስማ ተወላጆች ለኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት እየገበሩ መኖራቸውን አል ማክ
ሪዚ በታሪክ መጽሐፉ ያረጋግጣል ። እነዚህ አልፎ አልፎ የሚሸፍቱትም እንደ
ግራኝ አህመድ የኢትዮጵያን ነገሥታት አሸንፈው አገሪቱንም ወርረው አያው
ቁም ። በዚህ ፈንታ በተነሡ ቍጥር እየተሸነፉ ሲገብሩ ኖረዋል ። አንዳንድ ጊዜ
ባንዳንድ ውጊያ ላይ ቢቀናቸውም መደምደሚያውን ከመሸነፍና ከመገበር አል
ፈው አያውቁም ። ብዙ ጊዜም አንደኛው ሲሸፍት ወንድሙ ለኢትዮጵያ ንጉሥ
ታማኝ ሆኖ እየገበረ ያባቱን ግዛት እየተሾመ በሰላም መኖሩ በየታሪኩ ውስጥ
ጣልቃ ገብቶ ይታያል ።

በ፲፰፻፲፪ ዓ. ም. ግድም በአቡበከር ባራካት (የአህመድ በድላይ የወንድም
የልጅ ልጅ) ጊዜ መደበኛ ሥፍራው ከይፋት ወደ አዳል (ዳካር) ተዛውሮ በዳካር
ከትሞ ይኖር የነበረው የወላስማ ቤት ወደ ሐረርጌ ተዛወረ ። ይህ ዘመን (፲፰፻፲፪
ዓ. ም.) የግራኝ የወጣትነቱ ዘመን መሆኑ ነው ። በገዥዎቹና በተገዥዎቹ መካ
ከል ያለው ጠብና ጦርነት ሲጠፋ ሲለማ የኢትዮጵያ ነገሥታትም የሸፈተውን
ሲሽሩ የታመነውን ወንድሙን ሲሾሙ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት
ደረሱ ።

ወላስሞቹ በገዥዎቻቸው በኢትዮጵያ ነገሥታት ላይ ሸፍተው በተነሡ
ቍጥር እርዳታ የሚያገኙት ከማዶ ከሃይማኖት ወገኖቻቸው ከዓረብና ከግብፅ
ነው ። ለውጊያ የሚከተላቸውም ሕዝብ እላይ የጠቀስነው ቀደም ብሎ ባለው
ዘመን ወደእስላም ሃይማኖት ያስገቡትና በአምቻ በጋብቻ አብሮ በመኖር ያቀረቡት
የደንከል የአዳልና የኢሳ የሱማሌ አንዳንድ ጊዜም ከወዲህ ያለው የሐድያ የባሌ
የደዋሮ ተወላጅ ነው ። ይሁን እንጂ ከወዲህም ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ታማኝ
ሆኖ እነሱን የሚወጋ የአዳልና የኢሳ ሕዝብ አንዳንድ ጊዜም የዓረብ ተወላጅ ሳይ
ቀር መኖሩን ወደ ዋናው ታሪክ ስንገባ እንረዳለን ። የግራኝ አህመድ አሽናፊነት
የንጉሡ ተሸናፊነት ተስፋ አስቆርጦት በመጨረሻ እስኪከዳ ድረስ ከንጉሡ ጋር
ሆኖ በብዙ ቦታ የግራኝን ጦር ሲወጋ የኖረውን አውራይ ኡስማን ቤን ዳር አሊን
ለምሳሌ ያህል ማስታወስ ይቻላል ። እንደዚሁም ከወዲህ ተበደልሁ የሚል የክርስ
ቲያን መኰንን ከንጉሡ ሸፍቶ ወደነርሱ የገባና መሣሪያ የሆነ ይገኛል ። ለምሳሌ
ባዔ ናዖድ ጊዜ ሹመቱ ለሌላ ስለተሰጠበት ንጉሡን ከድቶ ለመሐመድ ኢብን አዝ
ሐር ያደረው የራስ ወሰን ሰገድ ወንድም ወናግ ዣን የሚባለው ይገኛል ።

ክርስቲያኖቹና እስላሞቹ ከሥር ከመሠረቱ ከሴምና ከካም ከኵሽ የፈለቁ
በዘር በቋንቋና በልማድ የተሣሰሩ ወገኖች እንደ መሆናቸው መጠን በመጋባት
በመፋቀር ፋንታ በዚያን ጊዜ በሃይማኖትና የሃይማኖት ሕግ በሰጠው ውሳኔ ፤
በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ልማድ ምክንያት ሁለቱ ወገኖች ስለተለያዩ በሰላም አብሮ
የመኖር ዘዴ መፍጠር አቅቷቸው ነበር ። በዚህ ፈንታ የነዚህ ትምክህት ክርስቶስ ፣
ቅዱስ ቦታ ኢየሩሳሌም ፤ ቅዱስና የሚታመነው መጽሐፍ ወንጌል ሲሆን ፤ የነዚያ
ነቢዩ መሐመድ ፤ ቅዱስ ሥፍራ መካ መዲናና ቅዱስ መጽሐፍ ቁራን ሆነ ። እግዚ

አብሔርን ሁለቱም ወገኖች በልዩ ልዩ ስም እያመለኩ ይሻሙታል ። በጦብ ጊዜም ሁለቱም ተዋጊዎች ድል ለማግኘት ይለምኑታል ፣ ድል ካገኙም በኋላ ሁለቱም ይመኩበታል ። ሁለቱም በየክፍላቸው ከኛ ጋር ነው ብለው ያምኑበታል ። እነዚህ እነዚያን "ተንባላት ፤ አረማውያን" እያሉ ሲያጕጥጡ እነዚያም እነዚህን "ነፍር፡ የማያምኑ ወይም በብዙ አማልክት (ሥላሴን) የሚያመልኩ" በማለት በቃልም በጽሑፍም የነበረው የመሰዳደብ ልማድ እስከ ጊዜያችን ዘልቆ ባለንበት ዘመን ላይ ፈጽሞ ባይጠፋም ቀዝቅዞ ይታያል ። ሁለቱ ወገኖች የሚያምኑበት ከክርስትና በፊት ያለው በኛ ዘንድ ብሉይ እየተባለ የሚጠራው የሙሴ ኦሪት የነቢያት ጽሑፍ፡ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ አቅም አላገኘም ።

ከዓፄ ይኩኖ አምላክ ዝምድ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ሙሉ ሥልጣን መያዝ ድረስ (፲፪፻፷፪ - ፲፭፻፲፯ ዓ. ም.) በሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ዓመታት ውስጥ በሁለቱ ወገኖች መካከል የፈሰሰው ደም ሳይደርቅ የተተከለው ቂም ሳይነቀል በራሳቸው ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ላይ ይኸውም ማለት ከግራኝ አነማሥ አሥር ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ገና ካፄ እስክንድርና ካፄ ናዖድ ዝምድ ያላረፈው ይማም ማኅፉዝ እንደ ንጉሥ የሚቆጠረውን ክርስቲያኑ ወናግ ዣን የገባለትን መሐመድ ኢብን አዝሐር የሚባለውን የበላይ መሪ አድርጎ ባዔ ልብነ ድንግል ላይ ሲነሣ ወደፊት በምዕራፉ ላይ በዝርዝር እንደምናነበው ተሸንፎ መሐመድ በደዋሮ እስላሞች እርዳታ በፈረስ ሲያመልጥ ማ[illegible]ዝ ከጦርነቱ ላይ በክርስቲያኖቹ የጦር አለቃ እጅ አንገቱን በሰይፍ ተመትቶ ሞተ ። ሟቹ ማኅፉዝም የግራኝ አህመድ ሚስት የድል ወንበራ አባት ነው ። የራሱ የአህመድ ግራኝ ታላቅ ወንድም ገራድ አቡን ቀደም ብሎ በተደረገ ጦርነት ውስጥ በራስ ወሰን ሰገድ እጅ ተገድሏል ።

ይኸን በመሰለ የጠብና የቂም መንፈስ መካከል ነው ግራኝ አህመድ ኢብራሂም ተወልዶ ያደገው ፤ አድጎም ክርስቲያኖቹን ሊበቀል የተነሣው ። አባቱ የገራድነት ማዕርግ ስላለው ግራኝ ከተራ ሰው አለመወለዱን እንረዳለን ። የናቱን ስም የኛ ታሪክ ነገሥት ሺምሽያ ብሎታል ። ለጊዜው ማረጋገጥ ያዳግታል ። የራሱን የግራኝን ሙሉና ትክክለኛ ስሙን ዓረብኛው አህመድ ኢብን ኢብራሂም ኤል ቃዚ (አዝማች) ሲለው ታሪክ ነገሥታችንም አህመድ ወልደ ኢብራሂም ብሎት ይገኛል ። የዛሬ የሐረርጌ ታሪክ ተመራማሪዎች በአባቱ የሐረር ተወላጅ በናቱ የሱማሌ ተወላጅ እንደሆነ ያረጋግጣሉ ። ዝርዝር ሁኔታው ወደፊት ይነበባል ።

ግራኝ አህመድ በተነሣበት ዋዜማ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ዝምድ ያላቋረጠው የእስላሞች ሁኔታ እያሰጋ ሲሄድ በተለይ እያደር ኃይል አግኝተው ከበረሃው ከአዳል አገር ከተማቸው ከዳካር ወደ ለምለሙ ወደ ሐረርጌ ከተዛወሩ በኋላ የማያቋርጥ እርዳታ ከሃይማኖት ወገኖቻቸው ከግብፅና ከዓረብ አገሮች እያደር በብዛት እያገኙ አስጊነታቸው እየታወቀ ሲሄድ ፤ ወደ ግብፅ ሡልጣን በየጊዜው ገጸ በረከት እየተላከ ዝምድና በመሻማት የተፈለገው ሰላማዊ ዘዴ ፤ ዓባይን ዘግቶ በጠብ የማስፈራራቱም መንገድ ምንም የደህንነት ዋስትና አለመስጠቱ ሲረጋገጥ ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ የክርስቲያን የውጭ መንግሥት ድጋፍ መፈለግና ማግ

ት ግዴታ ሆነበት ። ከዚህም በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። በበኩሉ በየወደቡ
ግዛትና በንግድ ከግብጾችና ከቱርኮች ጋር ዘወትር የሚጋጨው የፖርቱጋል መን
ሥት ደግሞ ለራሱ የግዛትና የንግድ ማስፋፋት ዓላማው የሚደግፈው በእስያም
አፍሪካም የክርስቲያን ጓደኛ ይፈልግ ነበርና በዚህ የመፈላለግ ሁኔታ አውሮፓ
ዊው የፖርቱጋል መንግሥትና አፍሪካዊው የኢትዮጵያ መንግሥት የየግል ፍላጐ
ቶቻቸው መርቶ አገናኛቸው ።

እንደ እውነቱ በክርስቶስ ባሕርይ ምክንያት በኬልቄዶን ጉባዔ የካቶሊክና
የተዋሕዶ ወገኖች በጠብ ከተለያዩ ወዲህ የቁስጥንጥንያው ንጉሠ ነገሥት ሔራቅ
ልዮስ አንድ ባሕርይ የሚለውን የእስክንድርያንና የኢትዮጵያን ፓትርያርክ አባ
ብንያምን አባሮ ሁለት ባሕርይ የሚለውን የተዋሕዶዎችን ዋና ጠላት አባ ቂሮስን
ከሾመ ወዲህ ፤ ይህ ጳጳስና የቁስጥንጥንያው አገረ ገዥ ማካውካስ የከሊፋ ኡመር
ጦር በአምሩ (ሙሉ ስሙ አመር በዲን ኡል አህሣ) እየተመራ በ፭ መቶ ዓ. ም.
ላይ መጥቶ ፪ ባሕርይ የሚሉት ከርሱ ተዋግተው ከተሸነፋና በዓረቦቹ (እስላሞቹ)
እርዳታ ሁለት ባሕርዮች (ካቶሊኮች) ተሸንፈው ያንድ ባሕርዮች (ተዋሕዶዎች)
መሪ ፓትርያርኩ አባ ብንያም ከግዞቱ ቦታ በዓረቦቹ እርዳታ ነፃ ወጥቶ ተመልሶ
በሊቀ ጵጵስናው መንበር ከተቀመጠ ወዲህ የኢትዮጵያም የግብፅም ክርስቲያኖች ፩
ባሕርይ ከሚሉት ካቶሊኮች ይልቅ አንድ አምላክ የ[illegible]ትን እስላሞች ያፈቀሩበት
ጊዜ ነበር ። ይኸም የፍቅር ስሜት ከእስክንድርያ ሥርዖ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ
ያን አባቶች ዘንድ ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች “ ፩ ባሕርይ
ብለው ክርስቶስን ከሚከፍሉት ፈረንጆች አንድ አምላክ የሚሉት እስላሞች ይሻ
ላሉ” በማለት ያዘወትሩ የነበረው አነጋገር እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

አሁን ግን እላይ እንዳመለከትነው የእስላሞቹ ሁኔታ እያሠጋው ሲሄድ ተዋ
ሕዶው የኢትዮጵያ መንግሥት ግድ ሆኖበት ከካቶሊኩ መንግሥት ከፖርቱጋል
ጋር ደብዳቤና ገጸ በረከት እየተለዋወጠ ዝምድናውን ማጽናት ዠመረ ። ይኸን
ንም በመጨረሻ የዓረብ አገሮች ጌታ የሆነው ግብጽን እንደ አው. ቀ. በ፲፭፻፲፯
ዓ.ም. የወረረው የቱርክ መንግሥት በሰሜን በኩል ከሐንጋሪና ከነምሳ ነገሥታት
ጋር በዚህ በኛ በኩል ደግሞ በስዊዝ በምጥዋ በሖርሙዝ (ፋርስ) በዲው (ሕንድ)
ወደቦች ከፖርቱጋል መርከበኞች ጋር እየተገናኘ ግዛትና ንግድ እየተፋለሙ በየጊ
ዜው ይዋጉ ነበርና እንደ አጋጣሚ በዚህ ጊዜ ኃይልም ተንኮልም ድፍረትም ጽና
ትም በፍጥረቱ የተዋሐደው ትንቢትንና ንግርትን ተንተርሶ በኢትዮጵያ መንግ
ሥት ላይ የተነሣው ግራኝ አህመድ እንደ ቀጠሮ ስለተገኘ የቱርክ መንግሥት ግብ
ፅን ከያዘ በኋላ ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ በበላይ ከሩቁ ከስጣንቡል ሥልጣኑ እየመ
ነጨ በቅርብ ያሉት የርሱ ታዛዦች የግብፅ የዘቢድ የአደን የሐድራሙት ፓሻዎች
ለግራኝ አህመድ የቅርብ ረዳቶች ሆኑ ።

በዚህ ምክንያት ቀድሞ ለወላስሞቹ አልፎ አልፎ ያላቋረጠው ዕርዳታ በዚህ
ኢትዮጵያና ፖርቱጋል ወዳጅነት በወጠኑበት ሰዓት የበለጠ ለግራኝ አህመድ በብ
ዛት ይደርስለት ዠመር ። ጦርነቱን ዠምሮ እየቀናው በሄደ ቍጥር በትእዛዝ

ወይም በቅጥር ከሚመጣው የእስላም ወታደር የበለጠ ከሀብታሙ የኢትዮጵያ ቤተ
መንግሥትና ቤተ ክህነት በዘረፋ የሚገኘው ተዝቆ የማያልቀው የደለበ የወርቅ
ሀብት እያደር እየሳባቸው ብዙ የግብፅ የዓረብ የቱርክ የፋርስ የሕንድ ፈቃደኛ ተዋ
ጊዎች ጥሩ ጥሩ መሣሪያ እየያዙ እየተሰበሰቡለት የመዠመሪያውን የወረራ እሽና
ፊነት ከማከናወን በቀር ድሉ ከጊዜያዊ ወራሪነት ወደ ነዋሪ ገዥነት እንዲያደር
ሰው በምክርም በጦርነትም ይረዱት ዠመር ።

ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግልና መኳንንቶቻቸው ይኸን በላያቸው ላይ
ከብዶ የመጣውን ጥቁር የጦርነት ደመና አገራቱን ለመውረር በግራኝ በኩል የሚ
ደረገውን ድርጅት የግራኝ አህመድን የወደፊት የበቀል ወረራውን የሰውዬውን
ጽኑ ተዋጊነት ከወደ መዠመሪያው የዋዜማ ጊዜ ላይ በትክክል አጢነው መፍትሔ
ውን አላበጁም ። ዓፄ ልብነ ድንግል ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ የጻፉት ደብዳቤ ሲን
በብ ሥጋታቸውና ለመደርጀትም ያላቸው ፍላጐት በአነጋገር ላይ ሠፍሮ በግልጽ
ይነበባል ። ነገር ግን በጠላቶቻቸው ግንባር የሚደረገውን የጦር ድርጅት እያሰለሉ
ማፍረሻ የሚሆን የወታደር ትጥቅ ለማደርጀት በትጋት መጣጣራቸው በተግባር
ላይ አይታይም ። ምናልባት እርሳቸውም ሹማምንቶቻቸውም ሁኔታውን መገንዘ
ባቸው መስጋታቸውና መፍትሔ ለማግኘት መመኘታቸው ሳይቀር የኖረው ልማ
ድና ዝቅተኛው የሥልጣኔ ደረጃ ሁሉንም አወሳስቦ ይዞት ይሆናል ። ተናጋሪና
መካር ቢኖርም አድማጭና ምክሩን በሥራ ላይ የሚያውል ገርውንና ዓይኑን
ከፍቶ የጠላቱን ሁኔታ የሚመለከት ተመልክቶ ከወደ መዠመሪያው ላይ ማጥፊያ
ውን የሚያበጅ ጽኑ የመንግሥታዊ አቅዋም እንዳልነበረ ይታያል ። ስለዚህ አደጋ
ውን እየተረዱት ምናልባት መፍትሔውንም ሳያጡት ነገር ግን የማያስቡትን
በሥራ ላይ ሳያውሉ የጦሩ መከራ ቀድሞ ደርሶባቸዋል ማለት ነው ።

ከዚህም ጋር ንጉሠ ነገሥቱ ለፖርቱጋል ንጉሥ ሲጽፉ በኔ ዘንድ ሰውና
ወርቅ እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተ ነው እንዳሉት ብዙ
ዘመን ረግቶ በኖረው መንግሥታቸው በሀብታቸውና በሠራዊታቸው ብዛት እነር
ሱም አባቶቻቸውም ካፄ ዓምደ ጽዮን ዠምሮ እያከታተሉ በሸፈቱት የእስላም ዙሪ
ቻቸው ላይ ባገኙት ባለፈ የሁልጊዜ አሸናፊነት ልባቸው ተጽናንቶ የመዠመሪያ
ውን የጠላትን ድርጅትና አሳብ በመረጃ እየተረዱ መሣሪያ የመሰብሰቢያውን
ወታደሩን በትጥቅ የማደርጃውን ምቹ ጊዜ በቸልታና በንቀት በመዝናናትና በዝን
ጋዔ አሳልፈውታል ።

ከመዠመሪያው ላይ ንግሥት እሌኒና ራሳቸው ንጉሡ ፈልገው በወጣኑት የወ
ዳጅነት መልእክት መሠረት የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል ቍጥራቸው ፲፫ የሚደ
ርስ የመልእክተኞች ጓድ በሮድሪጎ ደሊማ የበላይ መሪነት ወደ ዓፄ ልብነ ድንግል
ቤተ መንግሥት በላከ ጊዜ በዚህ ወዳጅነት ምክንያት የሚገኘውን ግናቸውንም
የመሣሪያና የወታደር ዕርዳታ ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ ያሉት የቤተ መንግሥትና
የቤተ ክህነት ሹማምንት ሳይገነዘቡ ከሩቅ አገር ከሊስቦን ቤተ መንግሥት ተነሥ
ተው ባሕሩን በመርከብ የብሱን በከብትና በእግር በስንት ድካም የመጡትን የፖር

ቱጋል ንጉሥ መልክተኞች በመልካም መስተንግዶ በቶሎ ተቀብሎ በደንብ በማነ ጋገር ፈንታ ተቀብሎ ለማነጋገር ብቻ አንድ ወር ደጅ አስጠንተዋቸዋል ። አነጋግሮ መልሶ ለመላክም የስድስት ዓመታት ጊዜ እንደፈጀባቸው ወደ መጽሐፉ አካል ገብ ተን ስናነብ ፤ ባቀባበል ረገድ ያለውን በሥነ ሥርዓት የታጠረውን ውዝግብ ስንመ ለከት ፤ በነርሱ ግንባር የተጸነሰው የግራኝ አህመድ ወረራ ተወልዶ ወረራው እያደገ እየበረታ ሄዶ ሊያስጠቃቸው የቻለው በቀጥታ በራሳቸው ቸልታና ንቀት መሆኑን እንገነዘባለን ።

ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል መልክተኞቹ በቤተ መንግሥታቸው በነበ ሩበት የስድስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የፖለቲካውንና የወታደርነቱን ጉዳይ ከዋናው መሪ ከሮድሪጎ ጋር ከመወያየት ይልቅ ያማልላቸው የነበረውን የመንፈሳዊ መጻሕ ፍት የማኅሌትና የቅዳሴ ጉዳይ በሁለቱ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለ ውን የሥነ ሥርዓት ልዩነት ለመረዳት ከካህኑ ከፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ጋር መነጋ ገሩ ያስደስታቸው ነበር ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የፖርቱጋል መልእክተኞች መር ከብ በመጠበቅና በሌላውም ሰበብ አስባብ የስድስት ዓመታት ጊዜ በኢትዮጵያ አባክነው በመጨረሻ ጠቅላላ ስምምነት ተደርጎ ከኢትዮጵያ ወደ አገራቸው በተ መለሱ ባመቱ ግራኝ አህመድ ጦርነቱን ዠምሮ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ከነራስ ደገልሃን ጋር ፤ በ፲፭፻፳ ዓ. ም. ከነወናግ ኀሮን (ሌላ ወናግ ዠን) ፣ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በመስከ ረም ወር ከነቢቶደድ ሠርጼ ጋር ፣ በዚሁ ዓመት በመጋቢት ወር ራሳቸው ንጉሡ ያዘ መቱትን ጦር ሽምብራ ኩሬ ላይ ሳይታሰብ ድል አድርጎ በታትኖ አገሪቱን መው ረር ዠመረ ። ንጉሡን ከነጦራቸው ከሸዋ እስከ ዝሆን ዱር (ጅባት ?) ከዝሆን ዱር እስከ ቤተ እምሐራ (ወሎ) ከዚያም እስከ ቤገምድር እስከ ጐጃም እስከ ላስታ እስከ ትግሬ ድረስ የሂዱበትን ዱካ በሰላይና በመሪ እግር በግር እየተከታተለ በመምታት ፈጽሞ እረፍት አሳጣቸው ። ልክ ጃፓኖች ባሜሪካኖች ላይ በፐርል ሐርበር እንዳ ደረጉት ንጉሡም መኳንንቱም የጦርነቱ ውርጅብኝ እንደ ድንገተኛ ማዕበል ሲደር ስባቸው ከመገረምና ከማዘን በቀር መፍትሔ የመፈለጊያው ጊዜ በዋዛ በፈዛዛ ስለ አለፈ ያለፈውም ጊዜ ተመልሶ በጦርነቱ ሰዓት ስለማይገኝ መከራውን ከመቀበል በቀር ሌላ ምንም ማድረግ አልቻሉም ።

በጠቅላላው የዓፄ ልብነ ድንግል መንግሥት በሠራዊት የግራኝን ጥርቅም ጦር በቍጥር ሰባ በመቶ በሀብት ዘጠና በመቶ ሳይበልጥ አይቀርም ። ካፄ እስክንድር ዠምሮ በኢትዮጵያ የተቀመጠው አሁንም በጦርነቱ ሰዓት ካፄ ልብነ ድን ግል ጋር ያልተለየው ፔድሮ ደኮቪልአ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ “ባንድ ዋሻ የተከመረው የንጉሡ የወርቅ ሀብት ዓለምን ሊገዛ ይችላል” ብሎ እንዳጫወ ተው አልቫሬጽ የጻፈውን በምዕራፉ ስንደርስ እናነባለን ። እስከዚያ ይህ ከሆነ እን ደዚህ የሀብትና የወታደር ከፍተኛ ብልጫ ያለው ያፄ ልብነ ድንግል መንግሥት አነስተኛ ጦር አነስተኛ ሀብት ባለው በግራኝ እንደምን ሊጠቃ ቻለ ብሎ መጠ የቅና መመራመር ተገቢ ሲሆን መልሱ በመጠኑ በቅድሚያ የተገለጸው ነው ።

ባለፈው እንደጠቀስነው መንግሥቱ በቸልታና በከንቱ የአስተዳደርና የሥነ

ISIC

ሥርዓት ውዝግብ ታጥሮ የግራኝን እንቅሥ ከጸጋሶ ለማጥፋት መሞከሩ እይታ ይም ። ጦርነቱ በተገመረበት ሰዓት የክርስቲያኖቹ ጦር የግራኝን ጦር የተቀበለው በንቀትና በቸልታ ሲሆን ግራኝ የገመረው ግን በንቃትና በትጋት በሙሉ ልብና በቆራጠኝነት ነበር ። የሠራዊት ቍጥር እንደ ሰማይ ከዋክብት የሀብት ብዛት እንደ ባሕር አሸዋ ቢበረክት ለማጥቃትም ይሁን ለመመከት ያን ጊዜም እንደዛሬ ተገቢ ትጥቅ ለውጊያ ጽኑ ፈቃድ ከሌለ ሁሉም ከንቱ ነው ። ያለዚያ ዓረቦች እሥራኤልን አሜሪካም ቬዬትናምን በቀላሉ ሊደመስሱ በቻሉ ነበር ። ባዩ ልብነ ድንግል የጦር ጕራ ታላላቅ መሳፍንት፣ ጕምቱ የሆኑ ስመ ጥር ሹማምንት፣ ቍጥሩ እጅግ የበረከተ ጅምላ ጦር ሲገኝ በግራኝ በኩል ግን የጦሩ ቍጥር ቢያንስም ባለው ጦር ላይ ከግዶ ከዓረብ፣ ከሕንድና ከፋርስ አገር የመጡ በጦርነት ዘዴ የበሰሉ በሰይፍ አመካከትና አመታት የሰለጠኑ አካላቸውን ውፍረት ሰውነታቸውን ድልጠትና ቅምጥልነት ያላጠቃው እንደነበሩባቸው የጦርነቱ አካሄድ በግልጽ ያሳያል ። የነዚህ የእወጋግ ተንኮልና ዘዴ ማጥቃቱ ከታየና ጦርነቱ ከተገመረ በኋላ ለመዘጋጀ በፍጹም ጊዜ አልነበረም ። ነገር ግን ጊዜው በከንቱ እየተዋጉ እየተማረኩ የማለቀያ ፣ እየተሸነፉ የመሸሺያ ወይም ለጠላት ገብቶ በሰይፍ በትር እየተገደዱ የመስለሚያ ጊዜ ሆነ ። ያመለጠውም የሰላምና የመዘጋጃ ጊዜ ተመልሶ ስለማይገኝ ባዩ ልብነ ድንግል ዘመን ሳይሠራበት የባከነው የሰላሙና የቸልታው ጊዜ ያስከተለው የፍዳና የመከራ ዘመን ላለንበት ወይም ለሚ፩፱፴ው ጊዜ ታላቅ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ከዚህ ከመግቢያው ይልቅ ወደዋናው የጽሑፍ ምዕራፎች ስንገባ በሰፊው እንረዳ ለን ። ከጐልያድ በፊት ከጐልያድም በኋላ ይኸን የመሰለው ጠላትን የመናቅ ስበብ ብዙ ጊዜ ጠላትን ጠቅሞ ራስን ሲያስጠቃ በዓለም ታሪክ ውስጥ በየጊዜው ታይ ቷል ።

ባገራችን ደጃች ካሣ (ዓፄ ቴዎድሮስ) በራስ አሊና በእቴጌ መነን ላይ ሸፍተው ቋራ የገቡ ጊዜ እቴጌ መነን ካሣን ለመውጋት ከጎንደር ወደቋራ ፊት ለፊት በተሳለፉበት ሰዓት ደግሞ «ይህ የፍየል እረኛ አያፍርም እኮ ከእ ጋር ንፎ ተፈታ ። እቴጌዪቱም እጭናቸው ላይ ተመትተው ተማረኩ ። «የፍየል እረኛ» ሲዋጋ ቆሟል» ብለው እየተገረሙ ጦርነቱ ከተገመረ በኋላ ወታደራቸው ተሸ ብለው የተሳደቡትን ለመበቀል ካሣ እቴጌዪቱን በዋሻ አስረው ባቁላ አስፈጨ ቸው ይባላል (1) ። ዓፄ ልብነ ድንግልም ግራኝን ለመውጋት በሠራዊታቸው ታጅ በው ወደ ሽምብራ ኩሬ ሲጓዙ ለሹማምንቶቻቸው «የግራኝ ጦር እምልጢችሁ ወደመጣበት እንዳይመለስ ተጠንቀቁ» ብለው ለምርኮኛ ማሠሪያም ብዙ ገመድ ተይዞ ነበር ። በኋላ መከራና ፍዳ ያስከተለው ታላቁ የሽምብራ ኩሬ ጦርነት የተገ መረው ይኸን በመሰለው የንቀት መንፈስ ነበር ። በኮራት ተጉዘው የመጡበትን መንገድ ተሸንፈው ተዋርደው እያዘኑ ሲመለሱ በልባቸው መገረማቸው የማይቀር

(1) ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሉ. ፋዚላ ያሳተመው ገጽ 9 ።

ነው ። ከድሉና ከሽሽቱ በኋላ የግራኝ ጦር ቤተ መንግሥታቸውን ሲያቃጥለው
በሩቅ እያዩ ማልቀሳቸውን በሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ።

ባለፉት ወራት ከየካቲት ወር ዠምሮ የተዠመረው ንቅናቄ እምብዛም ሊያስ
ደንቀን የሚችል አይመስለኝም ። ለንቅናቄው ምክንያት የሆነው ያስተዳደር ጉድ
ለት ፤ የፍርድ መዛባት ፤ የሥራ ፈት ብዛት ፤ የለማኝ መንጋጋት ባንድ ሀብታም
በሆነ አገር ላይ ሲታይ ለመነቃነቅ ምቹ ጊዜ በማማረጥ ይዘገይ ይሆናል እንጂ ለዘለ
ቄታ ዝም ብሎ እየተመለከተ በጽሞና የሚኖር ሕዝብ በዓለም ሊኖር አይችልም ።
በዚህ የተነሣ በመጨረሻ የደረሰው የኑሮ ውድነት ገፋፍቶ ሌሎቹን ሁሉ ጉዳዮች
ለመቀስቀስ ምክንያት ሆነ ።

የኑሮ ውድነትም ይበልጥ ያጠቃው የሕይወቱ ደረጃ ዝቅ ያለውን ተራ ሠራ
ተኛና ገበሬ ተራ ወታደርና ነጋዴ ብቻ ሳይሆን በተለይ ተምረውም ሳይማሩም በፍ
ጹም ሥራ ያጡትን የወንድና የሴት ወጣቶችን ነው ። ከዚህም ጋር የመሸታ ቤት
መበርከት የሴትኛ አዳሪ ብዛት የኅብረተ ሰቡን መልክ አበላሸው ። ለዚህ መፍ
ትሔ ፍለጋ በዩኒቨርሲቲ ወጣቶች በኩል አልፎ አልፎ የተደረገው ንቅናቄ ምንም
ያህል ውጤት ሳይሰጥ የጦር መሣሪያ የጨበጠው የጦር ሠራዊት ያደረገው ንቅ
ናቄ ግን ባንድ ወገን የአሳብን የንግግርን የጽሕፈትን ነፃነት ሲያስገኝ በሌላ በኩል
የሕገ መንግሥትን ለውጥ አስከትሎ የአስተዳደርን መሻሻል ለማብሠር ቻለ ።
ብሥራቱ ያለምንም ደም መፋሰስ መፈጸሙ ሊያስደንቅ ይገባል ።

አሁንም ይህ መልካም መስመር የያዘው የመሻሻልና የነፃነት ውጥን በሰላም
ቀጥሎ ከተረጋገጠ ሕገ መንግሥታዊ አገዛዝ ላይ ያረፈ እንደሆነ የንቅናቄው ባለ
ቤት ለሆነው ለጦር ሠራዊት ከዚህ የበለጠ ሊያኮራውና ሊያስመካው የሚችል
ነገር በፍጹም አይገኝም ። የዚህ ደንበኛው ትርጓሜ ጦሩ ባዲስ ለውጥ አዲስ የተ
ሻለ ሕይወት ከአዲስ የአኗኗር ዘዴ ጋር ለሕዝቡ አወረሰ ማለት ነው ። በዚህ ውር
ስና የነፃነት መብት ለመጠቀም የምንመኘን ሆነን የመገኘቱ ፈንታ የኛ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ ስለኑሮ ውድነት ከምናስበው የበለጠ ብጣም ውድና ምትክ ስለማ
ይገኝለት ስለራሱ ስለ ሰው ሕይወት ማሰላሰል አለብን ። ኢትዮጵያዊ የሆነው ሁሉ
ወንድማማች መሆኑ መዘንጋት እንደሌለበት በሁሉም አንደበት ተነግሯል ። እንግ
ዲያው የሥጋ ወንድማችን የሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ አጥፍቶ ሲገኝ ሕግና ፍርድ
ሊቀጣው ወይም ሊምረው ስለሚችል ለዚያ መተው አለብን ። ከዚህ ውጭ እንዱ
ምላጭ ስቦ የወንድሙን ሕይወት በዋዛና በቀላሉ ማሰናበት እንደሌለበት የማያ
ውቅ አለ ብዬ አልጠረጥርም ። ይህ ዓይነቱ እርምጃ ለመወሰድ ግዴታ የሚሆነው
ሰውዬው በቅድሚያ ለኢትዮጵያ ሕይወት ተቃዋሚነቱን ቆርጦ ሲነሣ ብቻ
መሆን አለበት ።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምንም ጥቃት የበዛበት ወይም ቁጭት የተጠራቀመ
በት ቢሆን ከሕግ ውጭ በራሱ እርምጃ በፈንታው ሌላውን ለማጥቃት ቢነሣ አጥ
ፊዎች በተባሉት እግር ራሱ ተመልሶ ከመግባቱ በቀር የሚጠቅመው ነገር የለም ።
አሁን ጥፋት ሆኖ የሚታየንም ከትውልድ ተያይዞ በውርስ የመጣ ጭምር እንዳለ

በት ሊታወሰን ስለሚገባ እርስ በርስ ከሚያባላን ይልቅ የሚያፋቅረንን መፈለጉ ጠቃሚ ነው ። በዚህ ዓይነቱ የውስጥ ሁኔታና የርስ በርስ ጠብ በ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. ግራኝ አህመድ ፥ በ፳ኛው መቶ ዓ. ም. ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ተጠቅመውበታል ። ዛሬ በሕይወት ያለነው ላገር ልማትና ጥፋት የሚሆነውን ለይቶ የማወቅ ከባድ ኃላፊነት አለብን ። ያኛው ጊዜ በሚያልቅበት አዲስ የንፃነት ጊዜ በሚጀምርበት ወቅት ከፍ ያለ ራሳችን በራሳችን የምንፈጽመው ቁጥጥርና ጥንቃቄ አለ ። ይኸውም ሳይመችን ተለማማጭ ፥ ሲመቸን ተሳዳቢ ፥ ሕግና የፖሊስ ክንድ ሲጫነን ሰላማውያን የነርሱ ክንድ ሲላላ ዘራፊዎችና ሁከተኞች ፥ በሌላ ቀን የምናከብረውን በክፉ ቀን የምናዋርድ በሌላው አጥፊነት የምንደሰት በራሳችን ንጽሕና የምንመካ መሆን የለብንም ።

መደምደሚያውን በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ሰው ትልቅ ሊባል የሚችለው በማናቸውም የጊዜ ወቅት የሕይወቱን ሚዛን ራሱ አውቆ ጠብቆ የሚገኘው ነው ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከ፲፭፻፲፱ እስከ ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. የደዋሮን (ከረዩ ጨርጨር አካባቢ) የፈጠጋርን (የረር ቡልጋ ምንጃር ያዳማ አካባቢ) የሸዋን ያን ጊዜ ገንዝ ዳሞት የሚባለውን የአምቦን የወሊሶን የጉራጌን የእናሴን የከምባታን አካባቢ ሁሉ እየመታ ካስገበረ በኋላ ከ፲፭፻፳፫ እስከ ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ድረስ ዛሬ ወሎ ያንጊዜ ቤተ አምሐራ የሚባለው አገር ጎጃምና ቤገምድር ከዚያም ተያይዞ የላስታና የትግሬ ወረዳዎች ሁሉ በየተራ እየተወረሩ መከራውና እልቂቱ እንደ ጽዋ ለሁሉም ሊዳረስ ቻለ ። አብያተ ክርስቲያናት ገዳማትና ብዙ የንገሥታት ከተማዎች እየተዘረፉ ተቃጠሉ ። ብዙዎች እየተዋጉ ሞቱ ፥ ብዙዎች እየተማረኩ የሰይፍ በትር በመፍራት ሰለሙ ።

ይሁን እንጂ ዘረፋው ቃጠሎው መታረዱ በቆየበት ፲፭ ዓመታት ውስጥ አሸናፊዎቹ ግራኝና የጦር አለቆቹ ከድሉ በኋላ ምንም ዓይነት ረዘም ያለ ዕረፍትና ሰላም ሳያገኙ የሸዋው የባሌው የዳሞቱ የጐጃሙ የቤገምድሩ የአንጐቱ የሽሬውና የሥራዬው የአከለ ጉዛዩ የሐማሴኑ ሕዝብ በዚያው በያዘው የሰይፍና የጦር መሣሪያ እየተዋጋ አንዱ ሲወድቅ ሌላው እየተነሣ ፥ አንዱ ተሸንፎ እምጥ ሲገባ ገብቶ እንደቀጠለ በመካከሉ በዚያ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ንግሥት እሌኒ በጠበኑትራው ሰዓት አባድፈው ጠይቀውት በነበረው እርዳታ መሠረት እነዚያ ፬፻ የፖርቱጋል ወታደሮች ዓፄ ልብነ ድንግል ርስቶፎሮስ ደጋማ መሪነት በዚሁ ዓመት መጥተው ባባታቸው እግር በተተኩት በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. በመስከረም ከሞቱ በኋላ በከበወጣቱ ንጉሥ ዓፄ ገላውዴዎስ ውስጥ በኅብረት በመዋጋት ግራኝ አህመድን በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. በዘንተራ አቀበት (ደንቀዝ) ሊገድሉት ቻሉ ። ግራኝ ከመሞቱ በፊት ጦሩን ይዞ በወጣቱ ንጉሥ ዓፄ ገላውዴዎስ ሠራዊት ፊት የተሠለፈ ጊዜ «እነዚህ ሳላድዳቸው የነበሩት እንደምን ዛሬ ደፍረው ከፊቴ ቆሙ» ብሎ ገርሞት ነበር ። በፊተኛው ጊዜ ትጉሕና ጦርጦራ ተዋጊ የነበረው ግራኝም በፋንታውና በተ

ራው የ፲፭ ዓመታት ያህል ኀዥነትና ኩራት አደንዝዞት ዓፄ ልብነ ድንግል ኀብተ ውበት በነበረው የንቀት ወጥመድ እሱም ገብቶ እንደሞተ ሲታይ በታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ ራሱን አዙርቶ ሌላውን የመናቅ ስሕተቱ ያለማቋረጥ ሲቀጥል መታየቱ አስገራሚ ነው ።

የሆነ ሆኖ ከአስፈሪው ከግራኝ ሞት በኋላ አልሞት ባይ ተጋዳይ ሆኖ ፲፭ ዓመታት ሲታገል የቆየው የክርስቲያን መንግሥት ተመልሶ ቆመ ። የቆመውም መንግሥት ምንም እንኳን በየጊዜው የርስ በርስ ጦርነት አዳክሞት የአውራጃ መከፋፈል ቢደርስበትም በጠቅላላው እየታገለ ነጻነቱን ይዞ እስከ ኢጣልያ ወረራ ደረሰ ።

ግራኝ አህመድ ከሞተ ወዲህ የግብጹም የዘቢዱም ፓሻዎች አዲስ ጦር ልከው የግራኝን ሞት ለመበቀል መንግሥቱንም መልሶ ለማቆም አልሞከሩም ። ከነርሱ በበላይ የሚገኘው ታላቁ የቱርክ ሱልጣንም በዚህ ጊዜ (፲፭፻፴ - ፲፭፻፶ ዓ. ም.) በአውሮፓና በሰሜን አፍሪካ ከጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ከሻርል ፭ ጋር ባንድ ወገን ከነምሳው መስፍን ከፌርዲናንድ ከሐንጋሪ ንጉሥ ከሉዊዝ ጋር በሌላው ወገን ደግሞ ከፋርስ ንጉሥ ከታሕማስፕ ጋር በከፍተኛ ደረጃ በግዛት ብዙ ክርክርና ጦርነት ስለአለበት የግራኝን የፊት አሸናፊነትና የኋላ ተሸናፊነት በጠቅላላው የኢትዮጵያን እንደገና የማንሰራራትና ተመልሶ የመቆም ጉዳይ በዝቅተኛ ስለሚመለከተው ሥራዬ ብሎ ሊያስብበት አልቻለም ። ግራኝን በመርዳት ስለ ኢትዮጵያ በቅርብ ያስብ የነበረው ዝቅተኛውና የቅርቡ የዘቢድ ፓሻ እንደዚሁም የየመን የአደን ፓሻዎች እነርሱም በቱርክ ውስጥ በየክፍለ ሀገራቸው የራሳቸው የተቆላለፈ ያስተዳደርና ያገዛዝ ችግር ስለአለባቸው ከፍ ያለ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ባዲስ መልክ ለማዝመት አልቻሉም ።

በዚህ ፈንታ ተዋሕዶዎቹ ኢትዮጵያውያንና ካቶሊኮቹ ፖርቱጋሎች በክርስቲያንነትና በወንድማማችነት መንፈስ ተረዳድተው ግራኝን ከአጠፉ በኋላ እርዳታውን አጣድፎ ባመጣው በዮሐንስ ቤርሙዴዝና በወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ባፄ ገላውዴዎስ መካከል የቆየው የተዋሕዶና የሁለት ባሕርይ የሃይማኖት ጠብ ተነሥቶ የተዘመረውን የመልካም ግንኙነት መንፈስ እንደምን እንዳደፈረሰው ከሥፍራው ስንደርስ በየምዕራፉ በዝርዝር እናነባለን ።

እንግዲህ በግራኝ ወረራ ምክንያት የመንግሥቱ መደበኛ ሥፍራ ከሸዋ ወደ ጐንደር ስለዞረ በደቡቦቹ የኢትዮጵያ አውራጃዎች ዘንድ የመገንጠል ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ ። ዓፄ ገላውዴዎስ የግራኝን ሞት ሊበቀል ተዘጋጅቶ ከመጣው ከግራኝ ተከታይ ከኑር ጋር ተዋግተው በሰማዕትነት በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ከአረፉ ወዲህ እንደዚሁም ኑር ርሳቸውን ገድሎ ወደ ሀገሩ ከተመለሰና ረሃብና በሽታ እርሱንም ወገኖቹንም ከፈጀ በኋላ የጐንደር ነገሥታት ባንድ ወገን ሥፍራው ስለራቃቸው በዚህም ላይ ከዓፄ ኢዮአሱ ቀጥሎ ካለው ጊዜ (፲፮፻፸፬ - ፲፮፻፺፰) ዠምሮ እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ መነሣት ድረስ እንደነራስ ስሑል ሚካኤል እንደነ ታላቁ ራስ አሊ እንደነራስ ጉግሣ ያሉ መሣፍንት እየተነሡ የነገሥታቱን ሥልጣን ስለአደከሙት ራሳቸውም መሣፍንቱ በሥልጣናቸው ከጐንደር ራቅ ያለውን እንደ ሐረር እንደ

ባሌ ያለውን አውራጃ ሁሉ መቆጣጠር ስለአልቻሉ ከግራኝ መንግት በፊት በኢት ዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት በነዓፄ ዓምደ ጽዮን በነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በራሳቸው ባፄ ልብነ ድንግል ሥር ይተዳደሩ የነበሩት የደዋሮ የባሌ የሐድያ የሲዳሞ የከፋ የወ ሊጋ አውራጃዎች ከዋናዪቱ ከኢትዮጵያ ተነጣጥለው ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ቍጥጥር ውጭ ሆነው በየባላባቶቻቸው ይተዳደሩ ገሩ ።

ሐረርጌም ራሱ የግራኝ አህመድ ዘሮች ይማም እየተባሉ ከነርሱ እጅ ይግሞ ሌሎች ነገዶች እየቀሙ አሚር እየተባሉ እየተለያዩም እየተሰበሰቡም አንዳንድ ጊዜ መደባቸውን ከሐረር ወደ አውሳ እያዛወሩ ሲገዙት ቆይተው በመጨረሻ በግብ ጾች እጅ እንደ አው. ቍ. በ፲፰፻፷፯ ዓ. ም. ሊወድቅ በቻለበት ዘመን አቅራቢያ ፣ አገሪቱ ከፉኛ ተለያይታ እውድቀት አፋፍ በተጠጋችበት ሰዓት እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ቴዎድሮስን ከቋራ አስነሥቶ የአንድነቷ መሠረት እንዲጣል አደረገ ።

ይኸን ወገንን የመሰብሰብ ንጉሠ ነገሥታዊ መብት የማስከበር ሥልጣን የግ ዛት ዘመናቸው ከአጠረው ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዓፄ ዮሐንስ ተቀብለው ከማድናት ጋር በዘመናቸው ኢትዮጵያን ለመውረር የመጡትን ግብጾች በ፲፰፻፷፯ ዓ. ም. እና በ፲፰፻፷፰ ዓ. ም. አሸንፈው የኢትዮጵያን ታላቅነት ካሳወቁ በኋላ ጕንደርን ካቃ ጠሉት ደርቡሾች ጋር ተዋግተው ስለኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ወሰን በመተማ ላይ ሕይወታቸውን በመሠዋት በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. ሞቱ ።

እንደዚሁም በዘመናቸው ዳግማዊ ምኒልክ የግራኝ እነሣሥ ባስከተለው ሰበብ በጕንደር ነገሥታት መራቅ ምክንያት የተነጣጠሉትን እላይ ስማቸውን የዘረዘር ናቸውን የደቡብና የደቡብ ምዕራብ አውራጃዎች በኃይልም በዘዴም በኃያላን የጦር አለቆቻቸው በነራስ ጐበና እያሳመኑ ከናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ቀላቅለው አዋሐዱ ። የዓፄ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለመገልበጥ ሕዝቡን ለመ ጅያ አድርጎት የነበረውን ሐረርጌን ግብጾች እንደለቀቁት በዚያው ምጥዋን በያዙ ማዊ ምኒልክ ተሽቀዳድመው በ፲፰፻፸፱ ዓ. ም. ጨለንቆ ላይ ግብጾች ሹመው ትተ ሀብታም የሐረርጌ ከተማና አውራጃ በዚያን ጊዜ ዓፄ ምኒልክ ባይዙትና እርሳቸው ነፃ በሚወጣበት ወቅት ሐረርጌ ከማን እጅ እንደሚወድቅ ወይም ምን ዓይነት ውዝግብ እንደሚያስከትል ለመገመት ከፍ ያለ ብልሀነትን አይጠይቅም ።

መላዋን ኢትዮጵያን ለመውረር የተነሣውን ኢጣልያን በዓድዋ ካሸነፉና የኢ ትዮጵያን ነፃ መንግሥትነት ለዓለም ከማሳወቅ ጋር የአገሪቱንም በር ለአሙሮ ሥልጣኔ ከከፈቱ በኋላ "እርስ በርሳችሁ ተጋግዙ ነፍስ አይግባባችሁ" ብለው ቀዋሚ ምክር ወርውረው አባቶቻቸው በሄዱበት ልጆቻቸውም በማይቀሩበት የሞት ጐዳና በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ሄዱ ። ይኸም ሁሉ ሆኖ በልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት ወራሹም አውራሹም አልታደሉም ። በዚህ ፈንታ ላገራቸውና ላባታቸው መንግ

ሥት ጽናት ሌት ተቀን ያስቡ የነበሩት ዳግሚት ወራሽ ንግሥተ ነገሥታት ዘው ዲቱ ካረፉ በኋላ አሁን በሕይወት ያሉት ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላገሪቱ በየጉዳዩ መስመር የሠሩትን በዝርዝርና በትክክል የምናውቀው ነው ። እንደ ደቡቡ አውራጃዎቻችን እንደ ሐረርጌ በግራኝ ወረራ ሰበብ መዠመሪያ በቱ ርክ ቀጥሎ በኢጣልያ እጅ የቆየውን የምጥዋንና የአሰብን ወደብ የማስለቀቁ ጉዳይ ላይ ዮሐንስም ላዔ ምኒልክም አስቸጋሪ የነበረውን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ባስከተለው የነፃነት መብት በመመርኰዝ ከኤርትራ ግዛት ጋር ነፃ አውጥ ተው ወደ እናት አገር ደባለቁ ። ኢትዮጵያ የጅቱ ዓመት ከባድ የኢጣልያ ወረራ ከገጠማት በኋላ የቃል ኪዳን ጓደኞቻቸውን የእንግሊዝን እርዳታ ይዘው የኢትዮጵ ያን ነፃነት መልሰው አቋቋሙ ።

የአፍሪካን መንግሥታት መሪዎች በመጋበዝ የቃል ኪዳኑ አንድነት በከተማ ቸው ላይ እንዲፈረምና እንዲመሠረት ፣ አዲስ አበባ የዚሁ ድርጅት መደበኛ ሥፍራ እንድትሆን ስለአደረጉ ይህ አድራጎት ላገሪቱ ዝና ከማትረፍ ጋር የፖለቲካ ጥቅም የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ፈጥሮላታል ።

ቸልታና ጠላትን መናቅ መዳከምን መከፋፈልን ካስከተለብን ከግራኝ አህ መድ ጦርነት ወዲህ ከላይ እነዓፄ ገላውዴዎስ እነዓፄ ሠርፀ ድንግል እነዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከታች ከዓፄ ቴዎድሮስ ዠምሮ የተነሡት እነዚህ ነገሥታት የጊዜ ውና የዘመኑ ወቅት ፣ የራሳቸው ችሎታና አቅም በሚፈቅደው መጠን ከፈጣሪ በዕ ድል ባገኙት የግዛት ዘመን ኢትዮጵያ ባፈራቻቸው የቀለም ምሑራን የጦርና የአስ ተዳደር ባለሥልጣኖች እየተረዱ ግራኝ አህመድ ከመሠረቱ አናግቶት የሄደውን መንግሥት በየጊዜው እየገነቡ የኢትዮጵያን ስፊ የግዛት ንብረትነት በአሁኑ ወር ድና ስፋት አሁን በሕይወት ለምንገኘው ሃይማኖትና ጉሣ ሳይለያየን ለማይገባው ኢትዮጵያውያን አስረክበው አስጨብጠውናል ። ነገሥታቱ በግዛት ዘመናቸው የሠሩት የጭካኔ ተግባር የፖለቲካ ስሕተት ወይም ያስተዳደር ጉድለት ቢኖር ወይም ሲፈጽሙት የሚገባው የልማትና የሥልጣኔ እርምጃ ባይሟላ በሠሩት ብቻ ተጽናንተን የፋንታችንን በማናቸውም የሥራ መስክ ተሠማርተን በዓይን ሊታይ በእጅ ሊዳሰስ በጕረቤት ሊሞገስ የሚችል የሥራ ፍሬ ማሳየት አለብን ።

ባለፈው አገሪቱን በማገልገል ተግባር የግል ምሥጋናው የነገሥታቱና የሹማ ምንቱ ብቻ አይደለም ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በጫማ እየተራመደ የጠላቱን ግን ባር እየመታ አንዳንድ ጊዜ የራሱን ግንባር ለጦር ፣ ባዶ እግሩን ለጠጠር የሚሰጠው ተራ ወታደር ፣ ሚችን እያናዘዘ የሚሸሸውን ተዋጊ እያወገዘ ከአገር ጠላት ጋር የሚ ያዋጋው ጳጳስና እጨጌ ቄስና መነኮሴ ፣ የቀን ሐሩር የሌት ቁር በመቻል እህሉን አምርቶ በረዥም ጉዞ ዱቄትና ማር በአህያ ጭኖ አንዳንድ ጊዜም ራሱ በትከሻው ተሸክሞ ለወታደር ስንቅ የሚያቀብለው ገበሬ ፣ ከአውሬ ከወንበዴ እየተከላከለ ከብዙ ኬላ ላይ እየተቀረጠ የመንግሥትን ግምጃ ቤት በቀረጥ የሚያከብረው ነጋዴ ፣ የጌታውን እርኮትና ጠመንጃ ተሸክሞ ከሰጋር በቅሎ ኋላ ላቡን እየጠረገ የሚከንፈው አሽከርና አገልጋይ ፣ አገልግልና መሶብ ተሸክማ ሙያዋን የምትጓ

ዘው ማታ በሰፈር ጌታዋ ሲያርፍ እርስዋ ባመንዋ ሳይረግፍ እግሩን አጥባ መብል
አብስላ ጌታዋን የምትመግበው ገረድ ፣ በዝርዝርም በድምርም ኢትዮጵያ ባሁኑ
ሁኔታ እንድትገኝ ሁሉም በተሰማራበት ያገለገሉት መስክ ድርሻውን ከፍሏል ።
ስለዚህ ከቱርኮቹና ከኢጣልያኖች ውጊያ በቀር እስካሁን በግናቸውም ሰበብ በማ
ንኛውም ጐሣና ሃይማኖት መካከል የተደረገው ጦርነት ሁሉ እንደ ቤተ ሰብ ጠብ
መቆጠር አለበት ። የክርስቲያኑም ወገን እርስ በርስ ሲዋጋ የኖረበት ታሪክ የሚዘ
ነጋ አይደለም ። ዋናው መሠረታዊ አሳብ በአሁኑ ጊዜ እንደሚታየው የወደፊቱን
ኑሮ ባዲስ የወንድማማችነት መንፈስ በጐሣም በሃይማኖትም በየግል ስሜት ሳይ
ታመሙ በመብትና በግዴታ ተተካክለው በሰላም እየሠሩ አብሮ የመኖሩ ጉዳይ ነው።

አባቶቻችን በዚህ ዓይነት ድካም ከዶሎ እስከ ምጥዋ ከማጂ እስከ አሰብ ድረስ
ያለውን በላዩ ማናቸውንም ሰብል ሊያበቅል የሚችለውን በውስጡ ሰፊ የማዕድን
ሀብት የታቀፈውን ስፋቱ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሐያ ሁለት ሺ ኪሎ ሜትር
ካሬ የሚደርሰውን ሰፊ መሬት አውርሰውናል ። ውርሱ በሀብት ረገድ ከፍተኛ
ግምት ያለው ስለሆነ አውራሽን የሚያስመሰግን ነው ። በውርሱ የዘር የጐሣ የሃይ
ማኖት የቀለም ልዩነት ሳይኖር በመሠረቱ አለቃና ምንዝር የሌለበት በኢትዮጵያ
ወሰን ክልል የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በትክክል ተካፋይ መሆን አለበት ። ለው
ርሱም ተገቢ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል ። ይኸውም ማለት ይኸን የጋራ ውርስ እጽ
ንቶ መያዙ የያዝነውን በዘመና[illegible]በብ እያለሙ በማናቸውም ኢትዮጵያዊና ኢት
ዮጵያዊት ላይ የድህነት መልክ እንዳይታይ መጣጣሩ ያሁኑና የመጪው ትውልድ
ፋንታ ነው ። ያለዚያ የውርሱ ባለቤትነት መስመሩ ከአስጊነት ወደ አሳዛኝነት ከዚ
ያም ወደ አዋራጅነት አቅጣጫውን እያሳበረ ሲሄድ የመስመሩ ፍጻሜ ከልማት
ዘሎ እጥፋት ላይ ሊቆም ይችላል ።

በዚሁ ጐን እንደ ግራኝ አህመድ ያለ ከየትኛውም ክፍል ማዕዘን ከውስጥም
ከውጭም ቢነሣ እነሣሡ ከማናቸውም ክፍል በስውርም በገሀድም ቢደገፍ ያሁኑ
የሃያኛው መቶ ዓመት ትውልድ ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን የነበረው የ፲ኛው ክፍለ
ዘመን ትውልድ ባሳየው ዝንጋኤና ቸልታ እነዚህም በሚያስከትሉት መከራና ፍዳ
ላይ መውደቅ የለበትም ።

በፊት እንዳፄ ልብነ ድንግል ቀጥሎ እንደ ራስ እንደ ግራኝ ወይም እንደ ራስ
አሊ እናት እንደ እቴጌ መነን ራስን ያለመንገዱ አክርሮ «እንዶ፡ት ያናሮ ከፊቱ
ተሠለፈ» ብሎ ጠላትን መናቅ ፣ ጠላት የጦር ትጥቁን ሲያደረጅ በቸልታ የራስን
ማላላት ሁኔታውን በገዛ እጅ በማዛወር ራስን አዋርዶ ጠላትን ማክበር ነው ።

ስለዚህ በሦስቱ መሪዎች ላይ በየተራ በየጊዜው የደረሰው ምሳሌ መሠረት
ሆኖ የዛሬዩቱ ኢትዮጵያ ከትናንትናዩቱ ኢትዮጵያ የምትማርበት የፊደል ሰሌዳ
በዚህ ዓይነት ተቀርጾ ሲታይ ሳትማርበት ብትቀር ኃላፊነቱ ጉዳቱ ከጸጸቱና ከን
ዴቱ ጋር ከልጆቿ ከኢትዮጵያውያኑ ጫንቃ ላይ አይወርድም ።

ለሰው ልጅ ኑሮ ማሻሻያ ለጦርነት ማስወገጃ የሚረዳ በብዙ ረገድ ከብዙ ሰው
አእምሮ እየፈለቀ ልዩ ልዩ ያስተዳደር ዘዴና ድርጅት ቢቋቋም በዓለም የሰው ልጅ

ኑሮ በኮሶና በማር ይኸውም ማለት በሰላምና በጦርነት የተበረዘ ሕይወት ከመሆን አልዘለለም ። የተባበሩት መንግሥታት በስም የተባበሩት በተግባር የተለያዩ ስለ ሆኑ የድርጅቱ አቅዋም በአለኝታና በተስፋ ላይ የተመሠረተ ውሳኔው ግን ብዙ ጊዜ ለምስክርነት በብዙ ቋንቋ ቢመዘገብም የአፈጻጸሙ ጉዳይ እንደ አየር ላይ ጢስ በኖ የሚጠፋ ነው ። ታናናሾቹ መንግሥታት ከታላላቆቹ ጋር በንግግርና በድምፅ አሰጣጥ ረገድ መብታቸው ምንም የተጠበቀ መሆኑ በቃል ኪዳኑ ጽሑፍ ላይ የሠፈረና የሚሠራበት ቢሆን በትክክለኛው አስተሳሰብ ታናናሾቹ እንደየመሪዎቻቸው የፖለቲካና ያስተያየት ዝንባሌ ለግላቸውም ላገራቸውም እንደሚያገኙት የእርዳታ መጠን በሚወስዱት እርምጃ ለኃያላኑ የጓደኛ ጭፍራነታቸውን ማሳየት ግዴታ ይሆንባቸዋል ።

ሁለት ታናናሽ መንግሥታት አንዱ በአጥቂነት ሌላው በተጠቂነት ጕራ ላይ ተሠልፈው እንደሆነ አንዱ ኃያል ከአጥቂው ጐን ሌላው ከተጠቂው ጋር ሆነው በማንሃታን አዳራሽ ከተከራከሩ በኋላ ሁለቱ ጠበቆች ከሁለቱ ባላጋራዎች የበቀለውን የየድርሻቸውን የመነሾ ፍሬ በውስጠ ስምምነት በየብስም በባሕርም በአየርም ላይ ተካፍለው ሲመገቡ ይታያሉ ። አጥቂ በአጥቂነቱ እንዳይረጋ አንደኛው ኃያል የመቃወሚያ የውሳኔ አሳብ "ሬዞሉሺን" አቅርቦ እንደሆነ ሌላው ኃያል የድምፁን አሰጣጥ አዝማሚያ ከተመለከተ በኋላ ብዙውን ድምፅ ባንድ ድምፅ በመሻር መብቱ በርሱ ተገን ውስጥ ያለው አጥቂ የአጥቂነቱን ሥራ እንዲቀጥል ይፈቅድለታል ። ይኸውም ሆኖ ኃያሉ ደጋፊ ባንድ በፖለቲካና በውስጥ አስተዳደር ለውጥ ምክንያት ሳያስጠነቅቅ ተንሸራቶ ወደጠላት የሚዞርበት ወቅት አለ ። የእሥራኤል መንግሥት ሲቆም የመዠመሪያው ደጋፊ መስኮብ ቀድሞ የሹመት ደብዳቤ በማቅረብ ወዳጅነቱን የገለጸ የዚሁ መንግሥት አምባሳደር ነበር ። በዚያን ጊዜ የፋይሳልን ኢራክ ፣ የፋሩክን ግብፅ ፣ የአብደላን ገርዳኒ ፣ ደጋፊዎች አሜሪካና እንግሊዞች ነበሩ ። ከፋይሳል መገደልና ከፋሩክ ውድቀት በኋላ አሜሪካና መስኮብ ሥፍራ ለሥፍራ ተቀያይረው ይህ ያሁኑ ጊዜ አሜሪካ የእሥራኤል መስኮብ የግብፅና የኢራክ ደጋፊ መሆናቸውን ያሳየናል ። ይህ ለምሳሌ የተጠቀሰው የመለዋወጥ ውዝግብ በማንኛውም ጊዜና መንግሥት ላይ ሊደርስ የሚችል የለት ያገር ጥቅምን ብቻ የሚከተል ዓላማ ነው ። አሁንም አሜሪካና ግብፅ ተመልሰው ተቀራርበዋል ።

ስለዚህ መደምደሚያውን በዚህ መግቢያ ላይ የተወሳው ሰላማዊና ወታደራዊ ሐተታ ተጠቃሎ ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት እንደነበረች አሁንም ለወደፊቱም ዓፄ በክንዱ ሆና እንድትኖር ያስገድዳታል ። የዓፄ በክንዱ ትርጓሜ በራሱ ክንድ የሚተማመን ኃይሉ ከራሱ የሚመነጭ ትጥቁን ራሱ የሚያደረጅ የጥንቱና የመካከለኛው ዘመን ጕልማሳ ባሁኑ ጊዜ የ፳ሺ. ዓመት ዕድሜውን የሚቆጥር ዘወትር የሚታደስ የአዛውንት ወጣት ፣ ዕድሜውን ሙሉ ዓለምን ለወረሩ ቄሣሮች ያልተንበረከከ ራሱ በቤቱ ሰውነቱን የማያስደፍር ክብሩን የማያስገሥሥ ቄሣር ነው ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ. ም.

ተክለ ጻድቅ መኵሪያ ፣

131C

ISIC

## ፩ኛ ክፍል

# በግራኝ አህመድ ወረራ ዋዜማ
# የኢትዮጵያ ጠቅላላ ሁኔታ

### ምዕራፍ ፩

### የአማራ ሕዝብ በይሁዳ አምላክ ንጉሣዊ መሪነት ሥልጣን መያዝ

ያገራችን ነዋሪው ጽሑፍ (ታሪከ ነገሥትና ክብረ ነገሥት) የአክሱም ነገሥታት ከንግሥተ ሳባና ከሰሎሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ የወረዱ እሥራኤላውያን በመሆናቸው በእሥራኤል አምላክ እንደሚያመልኩ በዝርዝር ጽፎት ይገኛል። ይኸንንም ቤተ መንግሥቱም ቤተ ክህነቱም አምኖበት የኖረ መሆኑን የማያውቅ የለም ።

በነኢኖ ሊትማን ፣ በነኮንቲ ሮሲኒ ትጋት የአክሱም ሐውልቶች በላያቸው ያለው ጽሑፍ በመሬት ተቀብረው ከተገኙት በነገሥታቱ መልክ ከተቀረጹት ልዩ ልዩ ገንዘቦች ጋር ጽሑፉ በየቋንቋው ተተርጉሞ ከተጠና በኋላ ነገሥታቱ ከደቡብ ዓረብ የመጡ አስታር ፣ አልመቀህ ፣ ሀወበስ ዘት ሐምያን ማሕረም በሚባሉ የጨረቃ የከዋክብት የባሕር የምድር አማልክት የሚያመልኩ ያደርጋቸዋል እንጂ በዳዊትና በሰሎሞን አምላክ በአዶናይ በያህዌ ወይም መጽሐፍ ቅዱስና ነቢያት "የሠራዊት ጌታ" በሚሉት በእውነተኛውና ባንድ አምላክ የማያመልኩ የእሥራኤል ቋንቋ የማይናገሩ መሆናቸውን በመግለጽ የላይኛውን የታሪከ ነገሥትንና የክብረ ነገሥትን አተራረክ አስተባብሎት ይገኛል ። በአክሱምና በየሐ በተገኙት የአማልክት ቤተ መቅደስ "ሙካሪብ - ምዙራብ" ላይ ወይም በየሐውልቱ ላይ እላይ የጠቀሰናቸውን የጨረቃና የከዋክብት አማልክት እያለ ከመጥራት በቀር በመቅደሱ ላይ ጽላተ ሙሴ የሚል አረታዊ ምልክት የለም ። እነዚህም አማልክት ዛሬም በሚገኘው በደቡብ ዓረብ ስማቸው በሳባ ጽሑፍ ተጠቅሶ ስለሚገኝ ወደ ኢትዮጵያ ስሜን የተሻገሩት ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግአዝያን በዚያው በደቡብ ዓረብ ከቀሩት ነገዶች ጋር ያላቸውን የዝምድና አንድነት ያረጋግጣል ። በዚህ ምክንያት የዛሬ ወጣትና አንባቢ አባቶቹ ከሚያምኑበትና ከሚተርኩት ከክብረ ነገሥት አጻጻፍ ወጥቶ በየሐውልቱና በየገንዘቡ ላይ በግልጽ በተገኘው ታሪካዊ ማስረጃ ላይ መመሥረት ግዴታው ሆኗል ። ነገር ግን ወደፊት በየምዕራፉ እንደምናነበው በነገሥታት ዝርዝር ውስጥ ጽዮን ገዛ ቤተ ፳ኤል ዙሉ ለጽዮን ጽዮን ሕግዚ የሚል ፳ኤላዊ ስም ስለሚገኝ በመካከሉ ፳ኤላዊ ሥርወ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ የገዛበት ዘመን ያለ ይመስላል ። ይኸንንም ሰፋ አድርገን በሚከተለው ምዕራፍ ውስጥ እናመለክታለን ።

የመጨረሻው አረማዊ የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ንጉሥ ስመ ጥሩው ዒዛና

(አብርሃ) ክርስትና ከመቀበሉ በፊት ለክብሩና ለጀብዱው ማስረጃ ይሆኑ ዘንድ በአሠራቸው ሐውልቶች ላይ ለጠላት የማይሸነፈው የማኅረም (የሠራዊቱው እም ላክ) ልጅ ይል የነበረውን ተወና ክርስትና ከተቀበለ በኋላ ማኅረምን ትቶ በኃይለ እግዚአ ሰማይ ወምድር ይል ገሠ (1) ። ክርስትና ከገባ በኋላ እርሱም ሌሎቹም ነገሥታት በመልካቸው በአስቀረጹት ገንዘብ ላይ የማኅረም ምልክት በነበረበት በጨረቃና በኮከብ ፈንታ መስቀል እየሳሉ ያስቀርጹ ገሥር ። ለዚሁም ማስረጃ የገንዘቦቹን ሥዕል ከፎቶው ላይ አገላብጦ መመልከት በቂ ነው (2) ።


በአረመኔነትም በክርስቲያንነትም ጊዜ የአክሱም መንግሥት ኃያልና ሥል ጡን እንደነበረ ከሐውልቶቹና ከገንዘቦቹ ጽሑፎች በላይ ማናቸውም ጸሐፊ ስለተ ረከው መደጋገም አስፈላጊ አይደለም ። ነገር ግን እንደማናቸውም ኃያልና ሥል ጡን መንግሥት የአክሱም መንግሥትም ከ፯ኛና ከ፰ኛው መቶ ዓ.ም. ወዲህ በዓረ ቦች መነሣትና ሰሜን አፍሪካን ከመያዛቸው ወደቦቹን ከመንጠቁ የተነሣ የውጭ ግንኙነት በማጣት ተዳከመ ። መዳከሙን ሲያዩ ቀድሞ ተገዥ የነበሩት ፈላሾች በጌዴዎን ልጅ በዮዲት መሪነት ተነሥተው አጠቁት ። ከፈላሾቹም በኋላ ዛጕዬ ዎቹ (የአገው ዘር) ተቀብለው ፈጽመው መንግሥቱን ቀምተው የመንግሥቱም መደብ ከአክሱም ወደ ላስታ ዞረ ። የዚህም ሁሉ ዝርዝር ታሪኩ በየመጽሐፉ ይገ ኛል (3) ።

በላስታ ዛጕዬዎቹ ከአሥረኛው እስከ አሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ከስተዳ ISIC ደሩ በኋላ በ፲፪፻፷፪ ዓ. ም. ላይ በአማራ አገር እየተማረ ያደገው ይኩኖ እምላክ መንግሥቱን ከዛጕዬው የመጨረሻ ንጉሥ ላይ ወስዶ ነገሠ ። መንግሥትን የአያ ያዙ መንገድ በትክክል የተጣራ ነው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ችግር ነው ።

ታሪከ ነገሥት ብዙ ዝርዝር ሳይሰጥ ይኩኖ እምላክን ከዛጕዬዎች በፊት የአክ ሱም መጨረሻ ንጉሥ ለነበረው ለድልነዓድ ፲ኛ ትውልድ ያደርገዋል ። አንዳን ዱም ዘጠነኛ የሚያደርገው አለ ። የነጋሢነቱን ዘውድና ዙፋን ከዛጕዬዎቹ ይኩኖ እምላክ የተቀበለው በጳጳሱ በአባ ጌርሎስ ፡ በሐይቁ መምህር በአባ ኢየሱስ ሞዓ ጸሎት በብፁዕ ወክቡር ርእሰ አበው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምልጃ መሆኑን ያረጋግ ጣል (4) ። በምልጃውም መካከል ሊቃቂው የዛጕዬው ንጉሥና ተቀባዩ ይኩኖ እም ላክ የተዋዋሉት ውል በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል (5) ።

ነገር ግን ብዙ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ከዚያውም በተለይ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ በአማራ አገር ከተሰፋ ኢየሱስና ከአዛዥ ጫላ ገረድ የተወለደው ይኩኖ እምላክ

(1) በማዕዙ ወልደ መሕርም ዘኢይትመዋዕ ሰዐር ይላል ። የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጕዬ ምዕ. 39
(2) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም . . . . . . ምዕ. 34
(3) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ምዕ. 68 - 70
(4) ታሪክ ነገሥት ገጽ 31 - 32 (በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የሚገኘው ቍ. 143) ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዋላስ ባጅ ያሳተመው ገጽ ምዕ. 26 - 27
(5) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ እምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 1 ። ገድለ ተክለ ሃይማኖት ፣
ምዕ. 24 - 27




አክሱማውያን በዘመናቸው ያሠሩዋቸው የመገበያያ ገንዘቦች (ሐተታውን በግልባጩ ተመልከት)

በመጀመሪያው መሥመር መያዳውን የአፈላስ በጀቲም ፊት ።

በሁለተኛው » » የገርስም » »

በሦስተኛው » » የአዛኤልና የዋዘባ » »

በአራተኛው » » ያልታወቁ » »

ISIC


በአምስተኛው » » » » »

በስድስተኛው » » መስቀል በጫፉ ያለበት በትረ መንግሥት ይዞ በዙፋኑ ተቀምጦ ዘውድ አድርጎ የሚታየው ነገሥ አረመሐ የሚለው የንጉሥ አርማሕ ከነግልባጩ ።

በሰባተኛው መሥመር የሐታዝ ከነግልባጩ ።

በ፰ኛው (በመጨረሻው) መሥመር ግማሹ የሐታገ የቀረው የእለ እጅ (እጅባሐ - ካሌብ ?) የጥዝና ናቸው ።

በ፩ኛው ፡ በ፪ኛው ፣ በ፫ኛው መሥመር ያሉት በግራኑ ጽሬው የጨረቃ ምል ክት ያደረጉት አረማውያን ፤ ከዚያ በታች ያሉት የመስቀል ምልክት ያደረጉት ክር ስቲያን ነገሥታት መሆናቸውን አንባቢ ይመልከት ፤



ዓፄ ይኩኖ አምላክ ለቤተ መስቀል ፥ ለቤተ ማርያምና ለደናግል የአባፎ ምድርን (ሠጠ) ጉልት የሰጡበት ታሪካዊ ጽሑፍ (ከአሀም ሽኔይደር ያገኘው)

ከዛጉዬው ንጉሥ መንግሥትን የወሰደው የአማራና የሸዋን ሰው ሰብስቦ ተዋግቶ መሆኑን ያረጋግጣሉ (1) ።

በእውነትም አንድ ንጉሥ ከላይ ካያትና ከባት የወረሰውን ዘውድ እንደልቡ የወደደውን የሚሾምበትን የጠላውን የሚሽርበትን የመንግሥት መሪነት በጳጳስ ልመና ወይም በመነኩሳት ምልጃ ለሌላው በተለይ ደግሞ ለማይወለደው ወገን በፈቃዱ አሳልፎ ይሰጣል ማለት በሰው ጠባይ በኩል ያልተለመደ ነው ። የዛጉዬ ዘር ለይኩኖ አምላክ ለመልቀቅ የተገደደበት ምክንያት እንደ ታሪክ ነገሥት እንጋገር የዛጉዬው ንጉሥ ከሰሎሞን ዘር አለመወለዱ ይኩኖ አምላክ ከቀድሞው ሰሎሞናዊ ነጋሢ ከድልነዓድ ዘር በመወለዱ መሆኑ በየመጽሐፉ ተጽፎ እናገኘዋለን ። ይኸውም ቢሆን መንግሥት ከሁለት መቶ ዓመት በላይ በእጃቸው ከቆየ በኋላ በሰላምና በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ምክር ከሰሎሞን ባለመወለዳቸው ብቻ ለዙፋኑ ተገቢ አለመሆናቸውን ራሳቸው ተገንዝበው ለመልቀቅ የሚችሉ አይመስልም ።

ነገር ግን ቀድሞ አገዎቹ በእክሱም አይለው መንግሥትን እንደወሰዱ አሁን ደግሞ በተራቸው አማሮቹ ባንድነት አብረው በአገዎቹ ላይ ተነሥተው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳትና በኢትዮጵያ የተሾሙትም ግብጻዊ ጳጳስ በዚህ ዘመን የተገኙትም ታላላቅ የቤተ ክህነት አባቶች እንደአባ ኢየሱስ ሞዓ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ራሳቸው የአማራ ተወላጅ በመሆናቸው ጭምር ለቀድሞዎቹ ነጋሢዎች ተቆርቋሪ ተወላጆቻቸውን ይተ[illegible]ላክን ደጋፊ መሆናቸውን ስለተረዱት መጠነኛ ጦርነት ካደረጉ በኋላ ፈጽመው በጦር ኃይል ከመደምሰሳቸው በፊት በተክለ ሃይማኖት አማካይነት ወደ ዕርቅ ድርድር ተቃርበው ይኩኖ አምላክ በጦርቅ ዙፋን ተቀምጦ በመላዋ ኢትዮጵያ እንዲነግሥ የዛጉዬው መስፍን በላስታ በብር ወንበር ተቀምጦ የብረት ነጋሪት እያስመቱ እንዲገዛ ተስማምተው በዚሁ አልቆ ይሆናል ። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በመካከል ሆነው ይኸን ስምምነት በአባትነት በምክር ስለአስፈጸሙ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የኢትዮጵያን ከሦስት አንድ ከንጉሡ መቀበላቸውን ታሪክ ነገሥቱ የሚያረጋግጠው በዚሁ ምክንያት ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፪

## የአማራ ሕዝብ ዘሩና ያለባቸው አውራጃዎች

እንግዲህ ስመ መንግሥቱ ይኩኖ አምላክ የክርስትና ስሙ ተስፋ ኢየሱስ በሺ፪፻፷፪ ዓ.ም. ዘውድን ከዛጉዬው ነጋሢ ወስዶ ሲነግሥና መቀመጫ ሥፍራውን በሸዋ ሲያደርግ በአሮጌው የአገው ሥርወ መንግሥት ፈንታ አዲስ የአማራ ሥርወ መንግሥት (ዲናስቲ) አገውኛ ተዳክሞ በነዋሪው በግዕዝ ፈንታም ለሕዝባዊ ንግግር

(1) Storia di Etiopia-Conti-Rossini ገጽ 317 - 318

አማርኛ ሲተካ በዚህ በአሥራ ሦስተኛው መቶ ዓ. ም. ላይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ መከፈቱን እንመለከታለን ።

ይኸም ሲሆን የአማራ ዘር ከወዴት መጣ ወዴት ነበረ የሚል ጥያቄ በአንባቢ ዘንድ እንደሚመጣ የታወቀ ነው ። ነጋሚው ይኸኖ አምላክስ አማራ ነው ወይስ ትግሬ ከላይስ የዘሩ ግንድ ሳባዊ ነው ወይስ እሥራኤላዊ የሚል ጥያቄ ስለሚደርስ ሁሉንም በአጭሩ ለይቶ ማመልከት የጸሐፊ ተግባርና ግዴታ ነው ። ጸሐፊም መሠረት ሊያደርግ የሚገባው በሰነድነት መልክ ለአስረጂነት በቂ የሆነውን ጽሑፍ ነው ። በዚሁ መካከል በየገድሉና በየድርሳኑ ውስጥ መሠረተ ቢስ የሆነውን የተረት አነጋገርና በቁም ነገር ላይ የተመሠረተውን ታሪካዊ ጽሑፍ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል ። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ታሪካዊ ምዕራፍ የተደረገ ወይም የደረሰ ነገር መኖሩ ሲታወቅ በቂ ሰነድ ስለማይገኝለት በሚያሳዝን አኳኋን እንደዚሁ ማለፍ ግዴታ ነው ።

በአክሱምና በዛጕዬ ዘመን የሆነውና የደረሰው ሁሉ እስከ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ በሐውልትና በገንዘብ ላይ በሳባ በግሪክኛ ፤ ከዓምደ ጽዮን ወዲህ በብራና ጽሑፍ ከግሪክኛ ፤ ከአረብኛ በግዕዝ እየተተረጐመ የተቀመጠው በአተራረክ የማይስማማው ቀኑና ዓመተ ምሕረቱ የማይገጥመው ብዙ ስለሆነ ሊገጥምና ሊገናኝ የማይችለውን ማስረጃ የሌለውን በመላ እየተረኩ አንባቢን ከማሳሳት እንዳለ መተው ከሁሉ የተሻለ ነው ። በመላ ጽፎ መጭን ትውልድ ከማጭበርበር ጉድሉውን ለመጪው ጊዜ ቢተውት ምናልባት በቀን ብዛት ሰነድ ወደፊት ተገኝቶ ሊሟላ ይችል ይሆናል ።

አሁን የአማራ ሕዝብ የመጣበትን የመሥመር አቅጣጫ እንፈልግ ። ከደቡብ ዓረብ ከክርስትና በፊት ኤርትራን ተሻግረው በስሜን ኢትዮጵያ ተበታትነው የተቀመጡትን የኛ የግዕዙ ታሪክ ነገሥት ነገደ ዮቅጣን ይላቸዋል ። ኖህ ለአዳም አሥረኛ ትውልድ ሲሆን ዮቅጣን ደግሞ ለኖህ ልጅ ለሴም አራተኛ ትውልዱ ስለሆነ ከደቡብ ዓረብ ወደ ኢትዮጵያ የተሻገሩት ነገዶች በሴም ሴማውያን በዮቅጣን ነገደ ዮቅጣን ይባላሉ ። ምንጩ በትክክል የማይታወቅ ነገር ግን አንዳንድ እንደዣን ሞሪዬ ያሉት የአገራችንም ጸሐፊዎች አለቃ ታዬም ብላቴን ጌታ ኅሩይም እንደሚተርኩት ባገር ነባር የሆነውን የኢትዮጵያን የነገደ ካሙን መንግሥት አሸንፎ የወረረውን የሕንድን ንጉሥ ራማን እነዚህ ነገደ ዮቅጣን አሸንፈው አገሪቱን ነፃ ስለአወጡ ነገደ አጋዕዝያን ነፃ አውጭዎች መባላቸውን ሳባ ትግሬን ሲይዝ ወንድሞቹ አባል የአዳልን አገር ኦፌር ውጋዴንን መያዛቸውን ይገልጻሉ (1) ። እንደዚሁም በዮቅጣን ልጅ በሳባ ሳባውያን ተብለው የነርሱ ገዥ ሴት ስትሆን ንግሥተ ሳባ እንደ ዒዛና ደግሞ ወንድ ሲገዛ ንጉሠ ሳባ ይባላል ።

ዛሬ የተጣራው ታሪክ በደቡብ ዓረብ ሳባውያን ፤ ሀበሳን ፤ ሂሚያሪት ፤ ሐሜረት እንደነበሩና ከነዚህ የሴም ወይም የዮቅጣን ነገዶች ውስጥ የኤርትራን ባሕር

(1) ዋዜማ — ብላቴን ጌታ ኅሩይ ም. 3 ገጽ 12 ። የኢት. ሕዝብ ታሪክ አለቃ ታየ ገጽ 31 - 38

ተሻግረው በኢትዮጵያ ሰሜን በያውራጃው ተሰማርተው የአክሱምን መንግሥት አቋመው ይተዳደሩ እንደነበረ ከማስረጃው ጋር ያረጋግጣል ። ማስረጃውም በአክሱም ሐውልቶች ላይ የሚነበበው የሳባው ፊደል የጨረቃ አምላካቸው ከነ ምልክቱ የነገሥታቱ አስተዳደርና ልማድ በደቡብ ዓረብ ከሚገኘው ጋር ፍጹም አንድ ወይም ተመሳሳይ በመሆኑ ነው ። የአማልክቱ ስም ማኅረም ፥ አስታር ፥ አልመቅሀ ሀውበስ . . . እያለ በደቡብ ዓረብ የተገኘው በኢትዮጵያ ሰሜንም ተገኝቷል (1) ።

እነዚህም ከልዩ ልዩ የሴም ነገድ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የሳባ ፥ የሀበሳን ፥ የሂሚያሪት ወገኖች ለትግሬና ለትግራይ ለአማራ ሕዝብ የነገድ አባት መሆናቸው በየመጽሐፉ ሲጻፍ የትኞቹ ለየትኞቹ አባቶች መሆናቸው እየተነጠለ በትክክል መጻፉ አስቸጋሪ ነው ።

ከዘመኑ ርቀት ከነገዱ ቅርንጫፍ ብዛት በየጊዜውና በየምክንያቱ ሕዝቡ ከመመሰቃቀሉ የተነሣ የትግሬው አባት ሳባ ነው የሐማሴኑ ሀበሳን ነው የአማራዎቹ ሂሚያሪት ነው ብሎ እየነጠሉ አፍ ሞልቶ መናገርም መጻፍም ያስቸግራል ። ያን ጊዜ ሀበሳት የሚባለው ዛሬ ሐበሻ መባሉ አያጠራጥርም ።

የሆነ ሆኖ የመሬቱ አቀማመጥ (ጂኦግራፊው) ሲታይ በደቡብ ዓረብ ፊት ለፊት የሚታየው የኢትዮጵያ ሰሜን ነው ። ስለዚህ የሳባ ወገኖች ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው በሐማሴን ፥ በአክለ ጉዛይ ፥ በአጋሜ የሀበሳን ወገኖች በአሳሆርታ በሐውዜን ሲሰማሩ በዓረብ አገር ሳሉ በስተደቡብ የሚኖሩት ሂሚያሪትና ሆሚሪት የኤርትራን ባሕር ከተሻገሩ በኋላ ሳባና ሀበሳን ከሠፈሩበት በስተደቡብ በኩል ያለውን ሰፋፊ አውራጃ ይዘው ስለሠፈሩ ሂሚያሪት ወይም ሆሚሪት የሚባለው ስያሜ በጊዜ ብዛት ትንሽ ፊደሉንና አባባሉን እየለወጠ መጥቶ በሂሚያሪት አምሐራ ተብሎ ይሆናል ።

እውነትም የአማሮች የመጀመሪያው መሠረታዊ አገር አምሐራ ሳይንትና ቤተ አምሐራ የሚገኝበት ሐይቅ ደብረ እስጢፋኖስ ፥ ግሼን መካነ ነገሥት ፥ እነ ተድባበ ማርያም እነአትሮንስ ማርያም የሚገኙበት ታላቅና ለምለም አውራጃ ነው ። በመካከሉ ከላዕላይ ግብፅ በሱዳን በኩል የመጡት የቢጋና (በጀያ) የአገው ሕዝብ እየተሰባጠረ ቢገባበትም በዚሁም ቢገምድር አገው ምድር ቢባልም በኋላ በጋሎች ሥሪት የተነሣ ወሎ ወረይሉ ወረሂመኑ እየተባለ ስሙ እየተለዋወጠ ተጠራ እንጂ ቀድሞ ከላይ ከሰሜን ትግሬ ከምዕራብ ቢገምድርንና ጐጃምን ከደቡብ ሸዋን ይዞ በመካከል ያለው ሁሉም በሙሉ የአማራ ግዛት ነበር ። በሸዋም የነበረው አማራ ከግራኝ ውድቀት በኋላ ጋሎች ከአፍሪካ ቀንድ በብዛት ወደ ላይ ወደ ባሌ ወደ አሩሲ ከመግፋታቸው በፊት ግዛታቸው በነዚህ አገሮች ላይ ሳይቀር የተስፋፋ ነበር ። ይህ ለአሁኑ የአማራ መንግሥት የመጀመሪያ ንጉሥ የሆነው ይኩኖ

(1) Storia di Etiopia pg. III-IV. Deutsche Axum expedition Inhalt voln Band IV pages 1-96.E. Glaser-Die Abessinier in Arabien pages 30-35 Y. Rye-kmans-Institution monarchique en Arabie...Chap. II-III. Pages 54-100 C. Rossini-Storia di Etiopia. Chap. V-VI.

አምላክ የተወለደው እየተማረ ያደገው በአማራ ግዛት በሚገኘው በታላቁ በሐይቅ በደብረ እስጢፋኖስ ገዳም መሆኑ በየመጽሐፉ ተተርኳል ።

ስለዚህ በፊተኛው በአክሱም ላይ አገዎች በርትተው ወይም በርክተው መንግሥትን እንደወሰዱ አሁን ደግሞ ይኸው እንደዚህ የበረከተው የአማራው ሕዝብ ኃይል ተሰምቶት በፊት ለወገኖቹ ለአክሱሞች ቀጥሎም ለአገዎቹ ሲገዛና ሥልጣንም እየተካፈለ ሲተዳደር ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ የዛጐዬን መንግሥት በአማሮቹ የቤተ ክህነት አባቶች በነአቡነ ተክለ ሃይማኖት በነአባ ኢየሱስ ሞዓ እየተረዳ ወሰደ ማለት ነው ።

ባንድ በጠቅላላ በአማራ ስም የሚጠራው ሕዝብ በቀን ብዛት እርሱ ደግሞ ብዙ ቅርንጫፍ እያበጀ የመሬቱን ስፋት ወርዱንም ቁመቱንም እያስፋፋ ከትግሬውም ከአገውም ከበጂያውም ከፈላሻውም በየወሰኑ ላይ በጋብቻና በኑሮ እየተከላለሰ ጐጃሜ ፣ ቤገምድሬ ፣ ስሜነኛ ሸዌ እየተባለ ተከፋፍሎ ይኖራል ። ይኩኖ አምላክና ተከታዮቹ እነዓምደ ጽዮን ፣ እነዘርዓ ያዕቆብ መቀመጫቸውን በዚሁ በሸዋ ማድረጋቸው በዚሁ የነገድ አንድነት የተነሣ ነው ።

ነገሥታቱ በሸዋ መንገዘ ተገለት የረር ቢቀመጡም በዘመናቸው ሁል ጊዜ የአማሮቹ የመገናኛ መደበኛ ሥፍራ ወደ ነበረው ወደ ቤተ አምሐራ እየሄዱ በዚያ በየስማቸው ቤተ ክርስቲያን መሥራት ያዘወትሩ ነበር ። በዚሁ ምክንያት ደብረ እግዚአብሔርን ሠይፈ አርዕድ ፤ መካነ ማርያም ዘርዓ ያዕቆብ ፣ አትሮንሰ ማርያም በዕደ ማርያም ፣ መካነ ሥላሴን በፊት ናዖድ የገሠረውን ልብነ ድንግል እያሠሩ አውራጃውን ማክበርና ማድመቅ እየሄዱ በየጊዜው መጐብኘት የአባቶቻቸውን አጽም በዚያ ማሳረፍ ይወዱ ነበር (1) ።

ወደፊት ከታሪኩ ላይ ስንደርስ በዝርዝር እንደምናነበው ግራኝ አህመድ በሺ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ዓፄ ልብነ ድንግል ራሳቸው ያዘመቱትን ጦር ሽምብራ ኩሬ (ገዳላ አጠገብ) ላይ ከዚያ አያይዞ ዋና ዋና የጦር አለቆቻቸውን እነራስ እስላም ሰገድን እነ አዝማች ተክለ ኢየሱስን ይልቁንም የመጨረሻውን ተስፋ ራስ ወሰን ሰገድን እያከታተለ በመውጋት ሁሉንም በየተራ (በሺ፲፭፻፳፪ - ፳፫ ዓ. ም. ላይ) ባሸነፈበትና ሳይታሰብ እየተከታተለ ይህ የመሸነፍ መከራ ባስጨነቀበት ጊዜ ንጉሡ ነገሥቱ «እንግዲህ ወደ አያቶቻችን አገር ወደ ቤተ አምሐራ እንሂድ» ብለው በመጨረሻ ከነበሩበት ከአዋሽ ወንዝ ዳር ያን ጊዜ ወጅ ዛሬ ወንጅ ከሚባለው ሥፍራ ወደ ዋሰል ተጓዙ (2) ።

ይኸም የአማራ ግዛት ምንም እንኳን ከተድሞው ስፋቱ ቢጠብ የጐንደር መንግሥት በነበረበት ዘመን ሁሉ በላዩ ላይ የከበረ ታላቅ ሰው የማዕርግ ስሙ ጸሐፊ

(1) ያዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ገጽ 123 ። ያዔ በዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ 119 - 130 (የኢትዮጵያ ታሪክ ከዔ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ 45) ። Informacao....Alvarez ምዕ. 94 - 95

(2) ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 281

ላም አንዳንድ ጊዜ ደጃዝማች ሌላ ጊዜ ራስ እየተባለ ሲገዛው ኖሯል ። ለርሱም በሥጋዊው ሹመቱ ላይ የተድባበ ማርያምን አልቅና ስለሚያርብ ያረጀው ከጐጃም ነጋሽ በላይ ከቤገምድሩ በታች ሆኖ መግዛቱን ለመግለጽ የጐንደሩ ነገሥታት ዜና መዋዕል የመኳንንቱን ደረጃ እገሌ ከእገሌ ቀጥሎ ይፈርዳል በማለት እንደዚሀ ይላል ። «. . . . . . ጐጃም ነጋሽ የአለቆች አሊቃ ነውና ከ . . . . በበላዩ ሆኖ ፣ የአማራው ጸሐፌ ላሕም በትረያርክ ነውና ከጐጃም ነጋሽ በበላዩ ሆኖ ፣ የቤገምድር አዝማች የወርወር ሊቀ ካህናት ነውና ከአማራው ጸሐፌ ላሕም በበላዩ ሆኖ ይፈርዳል ይላል . . . . .» (1) ።

ይኸንኑ የአማራ ግዛት በነገሤ ሱስንዮስ ዘመን ራስ የማነ ክርስቶስ በነገሤ በካፋ በነገሤ ኢያሱ ቋረኛ ዘመነ መንግሥት እነራስ ወዳጆ መዠመሪያ የደጃዝማችነት ቀጥሎ የራስነት ማዕርግ እንደያዙ ያስተዳድሩት ነበር ። ከራስ ወዳጆ ቀጥሎም ልጃቸው ራስ ጐሹ በዚሁ ግዛት ስለተተኩበት የአማራ አገር የእነራስ ወዳጆ ዘሮች እንደትክለኛ ባላባት ናቸው (2) ።

ራስ የማነ ክርስቶስ የዓፄ ሱስንዮስ ወንድም ነው ። ራስ ወዳጆ ለራስ የማነ ክርስቶስ የወንድሙ ልጅ ስለሆነ ፣ ባላባትነታቸው በንጉሣዊ ቤተ ሰብነት የተመሠረተ ነው ማለት ነው (3) ።

እስከ ግራኝ አህመድ መነሣት ድረስ በጣም ሰፊ የነበረው የአምሐራ ግዛት ከግራኝ ወረራ የለጠቀው የጋሎ[illegible]ነት በውጊያም በሰላምም ስራታቸው ስለበረከተ ከዓፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት (፲፭፻፺፱ - ፲፮፻፳፬ ዓ. ም.) ወዲህ በብዛት በነዋሪው የአማራ ሕዝብ መካከል ገብተው ከአማራው ሕዝብ ይልቅ እነርሱ ስለበረከቱበት ቤተ አምሐራ የሚባለው ነዋሪው የመጠሪያ ስሙ ቀርቶ ወሎ ፣ ወረ ይሉ ይባል ዠመር ። በነአባ ባሕርይ መጽሐፍ እንደተመለከተው ወሎ የከረዩ ልጅ የበረይቱማ የልጅ ልጅ ነው ። በበኩሉ ደግሞ ወሎ ቡኑን ወረ ጉራእን ወረ ኖሌኢሉን ወረ ከረዩን ወረ ኢሉን (ወረይሉ) ወረ ኖሌእሊን ይወልዳል (4) ።

እንደዚሁም ከግራኝ በፊትና በኋላ በተለይ በዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የጋሎች ሰሪት በነበረው በባሌ ፣ በአሩሲ በሌሎቹ አውራጃዎች በከፋ ፣ በጅማ በጠቅላላው የአማራ ሕዝብ በዝርዝር ሸዋ ፣ ቤገምድሬ ፣ ጐጃሜ ፣ አገው ምድሬ እየተባለ የሚጠራው አገር ለማቅናት አሊቃና ጭፍራ እየሆነ ወርዋሪ ትክለኛ በመባል ከገባ በኋላ ከጋላው ሕዝብ ጋር በመጋባትና በመዋለድ የተደባለቀውና በደም ተል

(1) «. . . . . ወበላዕሌሁ ጐጃም ነጋሽ እስመ መልአከ መላእክት ውእቱ ፣ ወበላዕሌሁ ጸሐፌ ላሕም ዘአምሐራ እስመ በትረያርክ ውእቱ ፣ ወበላዕሌሁ ቤገምድር አዝማች እስመ ሊቀ ካህናት ውእቱ ዘወርወር . . . . . .» የበካፋ ታሪክ ነገሥት ኢኛሲዮ ጉዪዲ ያሳተመው ገጽ 293

(2) ታሪክ ነገሥት ደጃች ኃይሉ እሸቱ (ከሸዋው አቤቶ አሊጋዝ ጋር) የሰበሰቡትና ፓሪስ በቍጥር 143 የተቀመጠው የእጅ ጽሑፍ ገጽ 260. 262. 281. 314 - 315

(3) ያዓፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ፔሬይራ ያሳተመው ( Cronica de susenyos-esleves pereira ) ምዕ. 2 ገጽ 78 ፤ 176

(4) ዜና ጋላ የሚባለው የአባ ባሕርይ መጽሐፍ ጉይዲ ያሳተመው (Corpusco ) ገጽ 223 - 231)

ቀት በሥጋ ልደት የተዋሐደው ብዙ ስለሆነ ዛሬ ይህ አውራጃ የዚህ ነገድ ነበር ብሎ ለመወሰን እስከሚያቅትበት ጊዜ ደርሷል ።

በዚህ የተነሣ በማናቸውም ረገድ በማናቸውም አውራጃ ላይ የባለቤትነት ሙሉ መብት ያላት ታላቂቱና ዘለዓለማዊቱ ኢትዮጵያ ስለሆነች እርሷን የሚያገለግልና በርሷ ሊመካ የሚችለው ኢትዮጵያዊ ማናቸውም አውራጃ ገንዘቡ ነው ። በታሪክ መልክ ነገዴ ከዚህ ሠፍሮ ነበር ፥ ከዚህ ሠፍሮ ወደዚህ ተዛወረ ማለት የማያካድ ታሪክ ስለሆነ ለወግ ይጠቅማል ።

## ምዕራፍ ፫
## የነገሥታቱ ዘር (እሥራኤላዊና ሳባዊ)

ባለፉት ምዕራፎች ስለ አማራ ዘርና ስለ አውራጃቸው ጽፈናል ። ዓፄ ልብነ ድንግል ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ እንግዲህ ወደ አባቶቻችን ወደ አያቶቻችን አገር ወደ ቤተ አምሐራ እንሂድ ማለታቸውና ያባቶቻቸው የነይሁዌ አምላክ አገር ቤተ አምሐራ መሆኑን ራሳቸውም አማራ መሆናቸውንም ጨምረን አመልክተናል ።

በይሁዌ አምላክ ተከታዮችና በደፋት ወላስማ ተወላጆች መካከል የተደረገውን የጦርነት ታሪክ በዘመኑ የጻፈው አል ማክሪዚ ነገሥታቱን የአማራ ነገሥታት በነርሱ ሥር የሚመራውን ሕዝብ በደፈናው አማራ ይለዋል (1) ።
ISIC

በዚህ ላይ ደግሞ እነዚህኑ የአማራ ነጋሥያን ታሪክ ነገሥቱ በብዙ ቦታ ላይ እንሱንም ከነርሱ በፊት የነበሩትን የአክሱሞችንም ነጋሥያን የእሥራኤል ዘር ያደርጋቸዋል ። ይሁዌ አምላክም የመጨረሻው የአክሱም ንጉሥ የድልነዓድ አሥረኛ ትውልድ እንደሚያደርገው በየመጽሐፉ ተመልክቷል ።

በታሪክ ነገሥት ላይ እንደተጻፈው የአክሱም ነገሥታት ከሰሎሞንና ከሳባ ከተወለደው ከምኒልክ የተወለዱ በሙሴ ሕግ የሚኖሩ እውነተኛውን አምላክ የሚያመልኩ ከማድረጉ በላይ ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለው የኪዳኑ ጽላት ከሰሎሞን ቤተ መንግሥት ተወስዶ ከምኒልክ ጋር መጥቶ አክሱም ቤተ ክርስቲያን መቀመጡ ብዙ ጊዜ ሲነገርም ሲጻፍ መቆየቱን ያላነበበ ወይም ያልሰማ አይገኝም ።

ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳልነው በአክሱም ሐውልቶች ላይ የተገኙት የሳባውም የግዕዙም ጽሑፎች የአክሱምን ነገሥታት ከደቡብ ዓረብ የመጡ በሳባና በግዕዝ የሚጽፉ የጨረቃን አምላክ የሚያመልኩ ስለአደረጋቸው ይኸን የላይኛውን ጽሑፍና እምነት አስተባብሎታል ። በራሳቸው የቋንቋ ጽሑፍ በሳባና በግዕዝ ላይ በዘመኑ የገነነውን ግሪክን ጨምረው ሲጽፉ አንድ ጊዜም የዕብራይስጥ ቋንቋ አልተጨመረም ። ማኀረም ሲነሣ የእሥራኤል አምላክ ያሕቤ ዝሆቫህ ወይም አዶናይ ተብሎ አልተጠቀሰም ፡ እያንዳንዱም ነጋሢ የቅርብ አባቶቹን በየሐውልቱ ላይ

(1) ከዓረብኛ ወደ ላቲን በፈ. ቁ. ሬንኑ የተተረጐመው ገጽ 21 - 40

ሲያወሳ ዳዊትን ሰሎሞንን እንኳን ሰሎሞንን የመጀመሪያ ንጉሥ የሆነውን ምኒልክን የሚያነሣ እስካሁን አልተገኘም ።


ይሁን እንጂ ከሐውልት ላይ ጽሑፉ አልተገኘም ተብሎ ነዋሪው ታሪክ ፈጽሞ ይሠረዝና ሌላ የታሪክ መሥመር ይተካ ማለት ያቸግራል ። ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ድልነዓድ የሁለት ሺ ዓመት ዘመን አልፏል ። በዚህ ረዥም ዘመናት መካከል የዙፋን መነጣጠቅ የነገሢ ዘር የመለዋወጥ ታሪክ ሊኖር ይችላል ። በአክሱም የነገሡት ነገሥታት የስማቸው ዝርዝር እንጂ ታሪካቸው የአብዛኞቹ በፍጹም እንደሌለን በትክክል መገንዘብ አለብን ። እንኳን ታሪካቸውን የስማቸው ዝርዝርም አልታወቀ ብሎ እነፕሮፌሰር ዲልማን እነድሮወ ቢቸግራቸው በሦስት ዓይነት ዘርዝረውት ይገኛል (1) ።

ስለዚህ ከወደ መጀመሪያው ዘመን ቀዳማዊ ምኒልክና ተወላጆቹ ላንድ ዘመን ተከታትለው ከነገሡ በኋላ በመካከሉ ከደቡብ ዓረብ የመጡ ከሳባ ወገን የሆኑ በማኅረም የሚያምኑ ከጽኤል የማይወለዱ መንግሥትን ለብዙ ዘመን መርተው ኀናንነትን ይዘው በየዘመናቸው ሐውልት እያሠሩ እስከ ዒዛና (አብርሃ) ድረስ ይሆናል ። ከዚያ ደግሞ ከክርስትና ወዲህ ዘራቸው ጽኤላውያን የሆኑ ምናልባትም ከፊተኞቹ ሰሎሞናውያን ነገሥታት የተረፉ መንግሥትን እንደገና ጨብጠው ይሆናል ። ወይም ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘራቸውን የሚቆጥሩ አዲስ የጽኤል ተወላጅነት ያላቸው መንግሥትን ወስደው እየመሩ እስከ ድልነዓድ ከደረሱ በኋላ እንደዚያው እንደተተረከው ከድልነዓድ ላይ ዛጕዬዎች ወስደው ይሆናል ።

ከቀዳማዊ ምኒልክ ዠምሮ እስከ አብርሃ ድረስ ከአብርሃ ዠምሮ እስከ ፳፪ኛው ንጉሥ እስከ አለ ዓሜዳ ድረስ አንድም ንጉሥ በጽኤል ነገሥታት ስም ፈጽሞም በጽኤላዊ ስም የሚጠራ አይታይም ። ነገር ግን ከድልነዓድ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ከዚሁ ከአለ ዓሜዳ ዠምሮ ያዕቆብና ዳዊት እንደዚሁም ያዕቆብና ቤተ ጽኤል የሚባሉ ነግሠዋል (2) ። ከድልነዓድ ዠምሮ እስከ እድም አሰግድ ድረስ በዛጕዬዎች ዘመን በስደት ኖሩ ከሚባሉት ውስጥ የድልነዓድ ልጅ እግብአ ጽዮንና ያዕቆብ የሚባሉ አሉባቸው ። ይኸም ለጽኤልነታቸው ምልክት ነው ። እንደዚሁም ኮንቲ ሮሲኒ ባዘጋጀው የነገሥታት ዝርዝር ውስጥ ሁሉ ለጽዮን ፡ ጽዮን ሕግዚ ጽዮን ግዛ የሚባሉ እንዳሉ ይገልጣል ። በአክሱም አካባቢ ከተገኙት የጥንት ገንዘቦች መካከል አንዱ የእሥራኤልን ስም ይዞ ይገኛል ። እርሱም ከካሌብ በኋላ ነው ተብሎ ተገምቷል ።

ስለዚህ ድልነዓድ በአክሱም መንግሥት በመጨረሻው በ፯ኛው ወይም በ፰ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት እሥራኤላውያን ነገሥታት ተመ

(1) የኢት. ታሪክ ንብያ አክሱም ዛጕዬ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕ. 33 Cat. Dillman (1855). Listes Royales Ethiopiennes -M-E Drouin (1882)
(2) የኢት. ታሪክ አክሱም ዛጕዬ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕ. 33 ከፊተኛው ላይ ፳፫ኛውን ፳፯ኛውን ፳፰ኛውን ተመልከት ፣



[illegible]

ሲያወሳ ዳዊትን ሰሎሞንን እንኳን ሰሎሞንን የመገርመሪያ ንጉሥ የሆነውን ምኒ. ከን የሚያነሣ እስካሁን አልተገኘም ።

ይሁን እንጂ ከሐውልት ላይ ጽሑፉ አልተገኘም ተብሎ ነዋሪው ታሪክ ፈጽሞ ይሠረዝና ሌላ የታሪክ መሥመር ይተካ ማለት ይቸግራል ። ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ድልነዓድ የሁለት ሺ ዓመት ዘመን አልፏል ። በዚህ ረዥም ዘመናት መካከል የዙፋን መነጣጠቅ የነጋሢ ዘር የመለዋወጥ ታሪክ ሊኖር ይችላል ። በአክሱም የነገሡት ነገሥታት የስማቸው ዝርዝር እንጂ ታሪካቸው የአብዛኛዎቹ በፍጹም እንደሌለን በትክክል መገንዘብ አለብን ። እንኳን ታሪካቸውን የስማቸው ዝርዝ ርም አልታወቅ ብሎ እንፕሮፌሰር ዲልማን እንድርወ ቢቸግራቸው በሦስት ዓይ ነት ዘርዝረውት ይገኛል (1) ።

ስለዚህ ከወደ መገርመሪያው ዘመን ቀዳማዊ ምኒልክና ተወላጆቹ ላንድ ዘመን ተከታትለው ከነገሡ በኋላ በመካከሉ ከደቡብ ዓረብ የመጡ ከሳባ ወገን የሆኑ በማጎረም የሚያምኑ ከጽኤል የማይወለዱ መንግሥትን ለብዙ ዘመን መር ተው ገናንነትን ይዘው በየዘመናቸው ሐውልት እያሠሩ እስከ ዓ.ዛና (አብርሃ) ደር ሰው ይሆናል ። ከዚያ ደግሞ ክክርስትና ወዲህ ዘራቸው ጽኤላውያን የሆኑ ምናልባ ትም ከፊተኞቹ ሰሎሞናውያን ነገሥታት የተረፉ መንግሥትን እንደገና ጨብጠው ይሆናል ። ወይም ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘራቸውን የሚቆጥሩ አዲስ የጽኤል ተወላጅ ነት ያላቸው መንግሥትን ወስደው እየመሩ እስከ ድልነዓድ ከደረሱ በኋላ እንደዚ ያው እንደተተረከው ከድልነዓድ ላይ ዛጉዬዎች ወስደው ይሆናል ።

ISIC


ከቀዳማዊ ምኒልክ ዝምር እስከ አብርሃ ድረስ ከአብርሃ ዝምር እስከ ፳፪ኛው ንጉሥ እስከ እለ ዓሚዳ ድረስ አንድም ንጉሥ በጽኤል ነገሥታት ስም ፊጽ ሞም በጽኤላዊ ስም የሚጠራ አይታይም ። ነገር ግን ከድልነዓድ ቀደም ብሎ ባለ ው ጊዜ ውስጥ ከዚሁ ከእለ ዓሚዳ ዝምር ያዕቆብና ዳዊት እንደዚሁም ያዕቆብና ቤተ ጽኤል የሚባሉ ነግሠዋል (2) ። ከድልነዓድ ዝምር እስከ እድም አሰግድ ድረስ በዛጉዬዎች ዘመን በስደት ኖሩ ከሚባሉት ውስጥ የድልነዓድ ልጅ አግብአ ጽዮንና ያዕቆብ የሚባሉ አሉባቸው ። ይኸም ለጽኤልነታቸው ምልክት ነው ። እን ደዚሁም ኮንቲ ሮሲኒ ባዘጋጀው የነገሥታት ዝርዝር ውስጥ ነሮሉ ለጽዮን ፡ ጽዮን ሕግዚ ጽዮን ግዛ የሚባሉ እንዳሉ ይገልጣል ። በአክሱም አካባቢ ከተገኙት የጥንት ገንዘቦች መካከል አንዱ የእሥራኤልን ስም ይዞ ይገኛል ። እርሱም ከካሌብ በኋላ ነው ተብሎ ተገምቷል ።

ስለዚህ ድልነዓድ በአክሱም መንግሥት በመጨረሻው በ፺ኛው ወይም በ፲ ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት እሥራኤላውያን ነገሥታት ተወ

(1) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ እስከ ይኩኖ ልምላክ ምዕ. 33 Cat. Dillman (1855). Listes Royales Ethiopiennes -M-E Drouin (1882)
(2) የኢት. ታሪክ አክሱም ዛጉዬ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕ. 33 ከፊተኛው ላይ ፳፫ኛውን ፳፯ኛውን ፳፰ኛውን ተመልከት ፤




ከየታሪክ ነገሥ...
ከዓፄ ከአክሱም ንጉሥ ከድልነ...
ያዕቆብ - ባሕ...



# ነገሥታቱ የዘር ግንድ

ሥት ተለቅሞ ባዲስ ዓይነት የተሠራ የይኩኖ አምላክ የዘር ሐረግ
ሐነዓድ - ማኅበረ ውድም - አግባእ ጽዮን - ጽንፈ አርእድ - ኑጉሽ ዮሐ - አስፍሕ -
ባሕር አሰግድ - እድም አሰግድ - ይኩኖ አምላክ እያለ ይወርዳል ።



ISIC

ላጅ ነው ማለት ነው ። ይኩኖ አምላክ የርሱ አሥረኛ ትውልድ ስለሆነ የርሱም ተወላጆች እነ ዓምደ ጽዮን እነ ዘርዓ ያዕቆብ እነ ልብነ ድንግልም ሸኤልነታቸውን የሚያረጋግጡት በዚሁ ምክንያት መሆን አለበት ።

ደንበኛው ታሪከ ነገሥትም በዚሁ የተነጣ «አንበሳ ውድም ድልነዓድን ወለደ ከርሱም ላይ መንግሥት ዛጕዬ ለሚባሉ ሸኤላውያን ላልሆኑ ለሌሎች ሰዎች ተላለፈ» ብሏል (1) ።

በዚህ ምክንያት ከሸኤል ዘሮች ሸኤላውያን ላልሆኑት ለዛጕዬዎቹ መንግሥት ተላልፎ ሲኖር አሁን ደግሞ በአማራ ሕዝብ ብዛትና ተዋጊነት በታላላቆቹ የቤተ ክህነት አባቶች በጳጳሱ በአቡነ ጌርሎስ (2) በሐይቁ መምህር በአባ ኢየሱስ ሞዓ በተከበሩት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት የሃይማኖትና የሞራል ድጋፊነት በይኩኖ አምላክ ጀግንነት ወደነዚያው ወደ ነገደ ሸኤል ተመልሷል ማለት ነው ።

ይህ አባቶቻቸው እነድልነዓድ እነአግብአ ጽዮን እነጽንፈ አርዕድ ተሰደውበት የነበረው መንግሥት በእጃቸው ስለገባ የይኩኖ አምላክ ተከታዮች ከመደሰት ጋር በመጠሪያ ስማቸው የእሥራኤል ዘር መሆናቸውን እሥራኤሎች ጥንት በነ ዳዊት ጊዜ የሚያመልኩባትን በክርስቲያኖች ዘመን ወደ ማርያምነት የተለወጠችውን ጽዮንን ሲያከብሩ ሲደግፉ ይታያሉ ። ያሁኑ ስያሜያቸውም ቀድሞ በአክሱም ጊዜ ኵሉ ለጽዮን ፣ ጽዮን ግዛ ከሚባሉት ጋር ተገናኝቷል ማለት ነው ። የይኩኖ አምላክ ልጅ አግብአ ጽዮን ተብሎ ሲሰየም እንግዲህ ይህ ነጋሢ መንግሥትን ከያዘ በዘመኑ ጽዮንን ይኽውም ማለት የጽዮንን ሕግ ያስገባል ያደረጃል ለማለት ነው ። መጠሪያ ስሙን አግብአ ጽዮን ከአሰኘ በኋላ ስመ መንግሥቱን ሰሎሞን ማሰኘቱ ዓፄ ዓምደ ጽዮን (የጽዮን ዓምድ) ስመ ጥሩው ተዋጊና ደራሲ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ (የያዕቆብ ዘር) መባላቸው በማስረጃ ላይ ማስረጃ ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤልና ለሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለቀሌምንጦስ ፯ኛ ደብዳቤ ሲጽፉ «እኔ ዕጣነ ድንግል ይኽም ስም የተሰጠኝ ክርስትና በተነሣሁበት ቀን ነው ። . . . በትረ መንግሥት በጨበጥሁ ጊዜ የዳዊትን ስም ከይሁዳ ቤት የመጣውን ስም ወሰድሁ ። የእሥራኤል ነገሥታት የዳዊት የሰሎሞን ልጅ የዓምደ ጽዮን የዘርዓ ያዕቆብ የበእደ ማርያም የናዖድ ልጅ በሥጋ ልደት» ማለታቸውን በሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ።

በሌላም አገር እንደሚደረገው በኢትዮጵያም ንጉሡ በአባቱ ኑዛዜ ወይም በመኳንንት ምርጫ ከነገሠ በኋላ እኛም ለዙፋኑ የቅርብ ተወላጅ ነንና እንንገሥ ብለው አገር እንዳያውኩ ወይም ቀንደኛ ተነሥቶ በነርሱ የነጋሢነት ደም እንዳ ይጠቀም ለጸጥታ ሲባል የነጋሢ ልጆች የሆኑት ሁሉ እየተጋዙ ባንድ ተራራማ ሥፍራ ይቀመጡ ነበር ። በአክሱሞች ጊዜ የደብረ ዳሞ የአምባ ጸለምት ተራራዎች

(1) አንበሳ ውድም ወለዶ ለድልነዓድ ዘእምኔሁ ተሐይደት መንግሥት ወተውኅበት ለካልአን እለ ኢኮኑ እሥራኤል ዘውእቶሙ ዛጓ ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 31
(2) ጽሑፉ ጌርሎስ ስለሚል እንጂ አንባቢ ቄርሎስ ሳይባል የቀረው በስሕተት እንዳይመስለው ፡

ለዚህ ጉዳይ ሲያገለግሉ ኖረዋል ። ከ፲፫ኛው መ.ቶ ጀምሮ እስከ ዓፄ ልብ ድንግል ዘመን ዋና የነገሥታት ልጆች ማስቀመጫ አምባ ግሼን (ቤተ አምሐራ) ነበር ። በዚህ ምክንያት ይኸው ተራራማ ቦታ አምባ ነገሥት ይባላል ።

ወደፊት በሥፍራው ስንደርስ እንደምናነበው የግራኝ አህመድ የጦር አሰቃ አምባውን ከቦ ተከላካዮቹን አሸንፎ የነገሥታቱን ተወላጆች የፈጀውን ታሪክ ነገ ሥቱ ሲተርክ የነገሥታት ልጆች በማለት ፈንታ እሥራኤሎች ብሏቸዋል ። ቃሉም በትክክል እንደዚህ የሚል ነው ፤ «በዚች በየካቲት ወር ግሼን አምባ ነገሥት ተሻ ረች ፤ ተበረበረችም ። በዚያ የነበሩትን እስራኤሎችንም በሰይፍ ገደሏቸው ። ከመ ካከላቸው ስለሃይማኖታቸው ወደ ባሕር የተወረወሩ አሉ» (1) ።

በተለይ ደግሞ ነገሥታቱ የሚመኩበት በጠቅላላው በእሥራኤልነታቸው ሳይሆን ከእሥራኤል ውስጥ ዳዊትና ሰሎሞን ከተወለዱበት የክርስቶስ እናት ማር ያም ከወረደችበት ከነገደ ይሁዳ መወለዳቸውን በማመን ነው (2) ። በዚህ ምክን ያት ፋት ዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ (፲፮፻፸፬ - ፲፮፻፺፱ ዓ. ም.) ኖሁ ሞዓ አንበሳ ኢያሱ ዘእምነገደ ይሁዳ ብለው እንደነበረው (3) በመጨረሻ ዓፄ ምኒልክ ሞዓ አን በሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እያሉ የመንግሥ ታቸው ዓይነተኛ ምልክት ያደረጉበት ምክንያት ከዚሁ ከጥንቱ ሲያያዝ የወረደ ውን እምነት መሠረት በማድረግ ነው ። ይኸውም እነሆ እስከ ጊዜያችን እስከ ቀዳ ማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ደርሶ ይቀጥላል ።

በዚህ ምክንያት የዙፋናቸውን ስም መንበረ ዳዊት ብለው ማንተማቸውን ወይም ኒሻናቸውን በሰሎሞን ስም ሰይመውታል ። የሚተዳደሩበትን ሕግና ሥር ዓተ መንግሥት ከእሥራኤል አገር ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከሰሎሞን ቤተ መንግ ሥት የመጣ መሆኑን ሲያመለክቱን ታሪከ ነገሥቱን አዘጋጂው እንደዚህ ይላል «. . . . . ከዕብነ ሐኪም ይኸውም ምኒልክ ከሚባለው ከሰሎሞን ልጅ ጋር ከኢየ ሩሳሌም የወጣውን የመንግሥት ሥርዓትና ሕግን እንጽፋለን» (4) ።

እነዚህ የእሥራኤል ዘርነት ያላቸው የአማራ ነገሥታት ዘራቸውን ከላይ ከነ ዳዊት ከነሰሎሞን ቢቆጥሩ ራሳቸው እሥራኤላውያን መሆናቸውን ቢያምኑም ቅዳሚንም ከእሑድ በፊት ቢያከብሩም ግዝረትን ቢያዘወትሩም የዝማሬው የማ ስረገጡ የጸናጽሉና የከበሮው የበገናው መሣሪያና ዘፈኑ ሁሉ የእሥራኤላውያንን ቢመስልም (5) በሌላ ልማድ በቋንቋ በፊደል በሃይማኖት በአሁኑ ጊዜ በዓለም ካሉት አይሁድ ተለያይተዋል ። በክርስቶስ ያላመነ ይሁዲና እሥራኤላዊም በነ

(1) «ወበይእቲ ወርኅ የካቲት ተሰዕረት ወተበርበረት ግሼን አምባ ነገሥት ወለ እስራኤልሰ እለ ነበሩ ህየ ቀተልዎሙ በሰይፍ ወቦ እለ ተወርወሩ ውስተ ባሕር በሃይማኖቶሙ ፡» ታሪከ ነገሥት ገጽ 94

(2) ኦሪት ዘኁልቁ ምዕ. 1 ፡ ኦሪት ዘፀ. ምዕ. 1 ፡ የዮሐንስ ራዕይ ምዕ. 5 ቁ. 5 ፡ ማቴ. ምዕ. 2 ቁ. 42 ፤

(3) ጉዶዲ ያሳተመው የአድያም ሰገድና የበካፋ ዜና መዋዕል ክፍል 7 ገጽ 266

(4) «ንጽሕፍ ሕገ ወሥርዓተ መንግሥት ዘወጽአ እምኢየሩሳሌም ምስለ ዕብነ ሐኪም ወልደ ሰሎሞን ዘውእቱ ምኒልክ ፡» ታሪከ ነገሥት ገጽ 25

(5) የዳዊት መዝሙር 47, 81, 149-150

ርሱ ዘንድ በጥብቅ የተጠላ ነው ። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያም ያሉት ዘራችንም ሃይማኖታችንም አይሁድ ነው የሚሉት ፈላሾች በነርሱ ዘንድ የተጠሉ ከመሆና ቸው የተነሣ በሸፈቱ ቍጥር በተለይ ባዔ ይስሐቅና ባዔ ሠርፀ ድንግል ዘመን የደረ ሰባቸው እልቂት ብዙ ነው (1) ።

እነዚህ ነገሥታት ከላይ ከሰሎሞን ዘር በመውረዳቸው ከደቡብ ዓረብ ከፈለ ቀው ለትግሬዎችና ለአማሮች የነገድ አባት ከሆነው ጋር ምንም እንኳን በሴሜዊ ነት በነገደ ዮቅጣንነት ቢዋሐዱም የገዥዎቹ ነገሥታትና የተገዥዎቹ ነገድ የተ ለያየ መሆኑ ይታያል ።

ይሁን እንጂ በዚያው በደቡብ አገር ሃይማኖቱም ዘሩም ይሁዳ የሆነ የሳባ መንግሥት ቆሞ ስለነበረና በዚሁ ምክንያት የሳባው ንጉሥ ይሁዳዊው ፊንሐስ በግዛቱ በናግራን ከተማ ያሉትን ክርስቲያኖች ስለፈጀ ክርስቲያኑ የአክሱም ንጉሥ ዓፄ ካሌብ ሄዶ የአይሁድን ንጉሥ ፊንሐስን ተዋግቶ ገድሎታል (2) ።

ስለዚህ ከደቡብ ዓረብ ወደ ኢትዮጵያ የተሻገረው የሳባ የሀበሳን የሚሚያሪት ሕዝብ ዘሩ ከአይሁድም ከሌላውም የሴም ዘር (ዓረብ) ተደበላልቆ በትክክል የይ ሁዲ ዘርነት ያለውንና የሌለውን አጣርቶ መለየት ስለማይቻል ሁሉም በብዛት አብሮ በኢትዮጵያ ሲኖር አማራነቱ ትግሬነቱ ይለይ እንደሆነ ነው እንጂ የዘሩ ልዩ ነት በጊዜ ርዝመት ጠፍቷል ። ስለዚህ ነገሥታቱ ከላይ ከሰሎሞን ዘራቸውን ቢጠ ቅሱም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የሚኖሩት የአክሱሞቹ በትግሬነት የአሁኖቹ ነጋሢዎች በአማራነት ስም ነው ።

አማራና ትግሬ በነገድ አንድነት በሌማድ በሃይማኖት ከመዋሐዳቸው የተ ነሣ የመንግሥቱ ዓምድ ሆነው ኖረዋል ። ከሌላም ነገድ የሚወለደው ሁሉ በኢት ዮጵያ ምድር የተገኘው ለመንግሥቱና ለንጉሠ ነገሥቱ በታማኝነት ያገለገለው ሁሉ የዘሩ ግንድና ዓይነት ሳይፈለግ የቤተ መንግሥቱንና የቤተ ክህነቱን ሥል ጣን ይካፈላል ። በዛጕዬዎቹ ዘመን ብዙ አማራና ትግሬ የሥልጣን ተካፋይ እንደ ሚሆን በፊት በአክሱሞቹ ጊዜ አሁንም በአማሮቹ ጊዜ የአገው ፣ የበጃ ፣ የጋላና የአ ዳል ዘርነት ያለው ሁሉ በነጋሢው ፈቃድ ሹመትና ማዕርግ ይዞ በኢትዮጵያዊነት መብቱ እንደሚኖር የታወቀ ነው ። ለዚህ ማስረጃው የዓረቡ ነጋዴ ሳሊህ ክርስት ናን ተቀብሎ በቤተ ክህነት አገልግሎት እያደገ ሄዶ አባ እንባቆም ተብሎ በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመን እጨጌ ተብሎ ከፍተኛውን የቤተ ክህነት ሥልጣን ይዟል ። ማናቸውም የበላይ ገዥ ንጉሥም ይሁን ንጉሠ ነገሥት በየትም አገር ቢሆን የመ ንግሥቱን ሥልጣን ለማካፈልና በደረጃ ለማሳደግ የሰውዬውን ታማኝነቱንና የልብ አገልግሎቱን ይመለከታል እንጂ የዘሩን ፣ የነገዱን ልዩነት አይመለከትም ።

እንግዲህ መደምደሚያውን ከላይ ከአክሱም ዘመን ተያይዞ በወረደው የዘር

(1) የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 23 ። ከዓ. ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ቴዎ. ምዕ 22 ።
(2) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም - ዛጕዬ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕራፍ 55 ።

ISIC

ግንድ መሠረት ክብረ ነገሥቱ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ንጉሥ ከተዳማዊ ምኒል ክና ከንግሥተ ሳባ ተወለደ የሚለው መሠረት ያለው ስለሆነ ይኵኖ እምላክና ተከታዮቹ ከላይ ከጫፍ ባባት ጳኡላዊ በእናት ሳባዊ ሆነው በቅርቡ የተወለዱበት ያደጉበት ይኸውም ማለት ከድልነዓድ እስከ ይኵኖ እምላክ ፲ ትውልድ ያሳለፉበት የትውልድ አገራቸው ሆኖ በተቆጠረው በቤተ እምሐራ አግሮች ናቸው ማለት ነው ።

ነገር ግን ብዙ ጊዜ የመካከለኛው ምሥራቅና የአፍሪካ ሕዝብ ከናት ወገን ይልቅ ላባት ዘርፍ ዋጋ መስጠት ስለሚወድ ነገሥታቱ ባባታቸው በሰሎሞን በኩል ያለውን ገነን አድርገው በመመካት ይጠሩበታል ። በዚህም ላይ እላይ እንዳልነው የዳዊት የሰሎሞን ነገድ የመጣበት ማርያም የተወለደችበት የነገድ አባት ከ፲፪ቱ ነገደ ጟኤል አንዱ ይሁዳ ስለሆነ በዚሁ የተነሣ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ የተባለው የነጋሢዎቹ የምልክት ርእስ ሆነ ።

ይሁን እንጂ በተለይ በፊደልና በሥነ ጽሑፍ ረገድ የእከሱም ያሁን የሸዋ ወይም የጐንደር ዘመን መንግሥት ኢትዮጵያ ስትጠቀም የኖረችው እስካሁንም የምትጠቀመው ከላይ በናት በኩል በወረደው ከደቡብ ዓረብ በመነጨው በሳባ ቀጥሎም በግዕዝ ፊደል እንጂ በመሠረቱ ዳዊትና ሰሎሞን ይጠቀሙበት በነበረው በዕብራይስጥ በፊደሉም በቋንቋ በሙሉ የተጠቀመችበት ጊዜ በታሪክ ውስጥ የለም ። የቀረው የኑሮ ልማድ ግን ከሁለቱም ወገን የመነጨ ልማድ በኢትዮጵያ እንዳለ ነው ። ክርስትናንም ፈጽሞ ሊያጠፋው አልቻለም ።

## ምዕራፍ ፬

## የንጉሠ ነገሥቱ ወሰን የሌለው ሥልጣን

ንጉሠ ነገሥቱ የዛሬው ሕገ መንግሥት በ፪ኛውና በ፫ኛው አንቀጽ እንዳጸደቀው ከሳባና ከሰሎሞን ዘር ከመጣው ከመጀመሪያው ንጉሥ ከቀዳማዊ ምኒልክ ፣ ከይኵኖ እምላክ ዠምሮ ያሉት የዚሁ የመጀመሪያው ንጉሥ ተወላጆችና ተከታዮች በጳጳስ ተቀብተው ሥርዓተ ንግሥ ተደርጎላቸው ጽራግ ማሠሬው ዘውዱን ከደፋላቸው መንበረ ዳዊት በተባለው ዙፋን ከተቀመጡ በኋላ የዛሬው ሕገ መንግሥት አጽድቆ እንደሚለው ክብራቸው ሳይቀነስ ማዕርጋቸው ሳይገሠሥ (ሳይሻር) ሥልጣናቸው ሳይደፈር እንደልባቸው ያስተዳድራሉ ።

አንዱ ንጉሥ አባቱ ሞቶ በአባቱ ኑዛዜ ወይም በባለሥልጣኖች ምርጫ ከነገሠ በኋላ እንደልቡ ይሾማል ፣ ይሽራል ፣ ያስራል ፣ ይፈታል ፣ ይገድላል ፣ ቅጣት ይቀንሣል ፣ ይምራል ። በዳዊትና በሰሎሞን መንግሥት እንደኖታን ያሉት በምክር ካልገሠጹ በቀር ነጋሢዎቹ ምንም በሥልጣናቸው ወሰን እንዳልነበረበት በነዚህም በኢትዮጵያ ነጋሥያን ዘንድ ዓቃቤ ሰዓቱ ብሕትወደዱ እጨጌው ጳጳሱ ወይም እናቱ በምክር ካልመለሱት ወይም የራሱ አእምሮ ካልገታው በቀር ንጉሡ የፈቀደ

ውን ለማድረግ የሚያግደው ሕግና ምክር ቤት የለም ። ይህ የ፲፰ - ፲፱ መቶኛ ዓመት እንኳን ሥልጣኔ በአልነበረበት በኢትዮጵያ ሥልጣኔና አስተዳደር በተሻሻለበት በአውሮፓም በምሥራቅም በወደ ትም ያሉት ነገሥታት የልባቸውን የሚሠሩበት ዘመን ነው ።

በዚሁ አያያዝ መሳፍንቱ ሳይቀሩ እንደልባቸው ሲኖሩ ከንጉሠ ነገሥቱ በቀር ቀጭ ስለሌለባቸው በፈረንጆች ዘንድ «መስፍኑ ሲያጠፉ የእልፍኝ አሽከሩ ይመታል» እየተባለ ይተረታል ። የኛ መሳፍንት ግን ይኸን የመሰለ የመንቀባረር ዕድል እንዳይገኖማቸው የሕፃንነታቸው ጊዜ አልፎ የወጣትነታቸውና የመሞላቀቂያቸው ጊዜ ሲደርስ ወዲያው በግዞት ተይዘው ወደ ግዞቱ ተራራ ወደ አምባ ግሼን ስለሚላኩ በልጅነታቸው ያልነገሡት ወይም አባታቸው በርኅራኄ ያልተዋቸው መሳፍንት ሁሉ በነፃነት ረገድ በእውነት የኑሮ ዕድላቸው ከመኳንንት ልጆች ያነሠ ነው ማለት ይቻላል ። ያንን ሁሉ የጭቆናና የግዞት ጊዜ ቁጭታቸውን የሚወጡት ከነገሡ በኋላ በነጋሢነት ሥልጣናቸው እንደልብ በመጠቀም ነው ።

በዚህ ዓይነት ንጉሠ ነገሥቱ በዙፋኑ ከተቀመጠ በኋላ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ያለው ሕዝቡም ሀብቱም እንደግል ንብረቱ ሆኖ ይቆጠራል ። ከላይ ከዳዊት ከሰሎሞን ዘር የወረደ እግዚአብሔር ቀብቶ ያነገሠው ተብሎ ስለሚታመን የሚያደርገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚደረገው ስለሚቆጠር ለመቃወም የሚደፍር በብርቅ ነው ። የደፈረውም ቢኖር ይህ ደፋር ለሞት ወይም ለከፍተኛ ቅጣት የተመደበ ነው ።

ዓፄ ዓምደ ጽዮን የዓፄ ይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ ያፄ ውድም ረዓድ ልጅ ነው ። በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ነግሦ ፲፭ ዓመት ኢትዮጵያን ሲገዛ በዘመኑ ብዙ ጠቃሚ ነገር ሠርቷል ። ሊጠፋ የነበረውን የቤተ መንግሥት የሥርዓትና የታሪክ መጻሕፍት እያሰበሰበ እንዲጻፍ ያደረገ በወላስማው ባላባቶች በሐቀዲንና በነስረዲን መሪነት የደቡብና የምሥራቅ ባላባቶች ባንድነት አብረው ክርስቲያናዊውን መንግሥት ገልብጠው የእስላም መንግሥት ለማቆም ሊወጉት በመጡ ጊዜ በብርታት ተዋግቶ ብማሸነፍ መንግሥቱን ከውድቀት አድኗል ።

ነገር ግን እላይ እንዳመለከትነው ለፍላጎቱ ለሥልጣኑ ወሰን እንደሌለው ሁሉ ግማሹ በዘመኑ የአባቱን ዕቁባት አስቀመጠ ሲለው ሌላው በሁለት እትማማች አመነዘረ ፤ አንዳንዱ እኅቱን ደፈረ ብሎ መታማቱን የዘመኑ ታሪክ ነገሥት ይገልጻል (1) ። ይሁን እንጂ በርከቶ በይፋ የተወራው የአባቱን ሚስት አግብቷል የሚለው ስለሆነ በዚህ ዘመን የነበሩት የተከበሩት እጨጌ ፊልጶስ ይኸን የመሰለውን ወሬ እየሰማሁ ዝም ብዬ አልቀመጥም ብለው ወደ ንጉሡ ሄደው «በእርግጥ የአባትህን ሚስት አግብተሃልን ?» ብለው ቢጠይቁት «አዎን እርሷን ካላገባሁ መንግሥትህ አይጸናም ብለው ካህናቱ ስለመከሩኝ አግብቻለሁ ። ያውስ የማትወልደኝን ያባቴን ሚስት ባገባ ምን ኃጢአት አለበት» ብሎ በድፍረት መለሰላቸው ። እጨጌውም

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 31 ። የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 8 ።

«ይኸን የመሰለ ምክር የሰጡህ ጠንቋዮች የሐሰት አባት (ዲያብሎስ) ያስተማራቸው መሠርያን ናቸው» ብለው ቢመልሱ ንጉሡ እጨጌውን በተፈ አስደብድቦ ራቁታቸውን አጽማቸው እስኪታይ ድረስ አስገርፎ ወደ በረሃ አገር በግዞት መላኩን ገድለ ፊልጶስ በዝርዝር ይተርካል (1) ፡፡

ከርሳቸውም በታች አባ አኖርዮስ የሚባሉት የሸዋ መምህር በዚሁ ነገር ንጉሡን ስለአወገዙ ደማቸው እስኪንጠባጠብ ድረስ በንጉሡ ትእዛዝ ገበያ ለገበያ እያዞሩ የንጉሡ ወታደሮች መግረፋቸውን ታሪክ ነገሥት ያመለክታል (2) ፡፡

በዚህ ዓይነት ንጉሡ ነገሥት እንኳን በቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖችና በመሃይምን ዜጎቹ ላይ በመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተቀመጡት በተከበሩት በእጨጌው ላይ የመግረፍም የማሠርም ቢያሰኘውም ኖሮ የመግደልም ሥልጣን እንዳለው እንገነዘባለን ፡፡ ይኸንንም ሥልጣን ከመቀበሉ ከመንገሡ በላይ የሚያረጋግጥለት በርሱ ሥልጣን ውስጥ ያሉት እርሱ በሾመት የሚያሳድጋቸው መኳንንትና በነርሱ ውስጥ በንጉሡ ትእዛዝ መኖሙን እየገኘ የሚተዳደረው የወታደሩ ኃይል ነው ፡፡

በመካከለኛው ዘመን ያለ የሌላው አገር ንጉሥና ንጉሠ ነገሥት በየግዛቱ እንደሚሰማው በኢትዮጵያም አፄ ዓምደ ጽዮን የኢትዮጵያ ምድርና በመሬቱ ላይ የሚገኘውን ሁሉ እንደግል ንብረቱ መቁጠሩን የምንረዳው እነሆ አቡነ ፊልጶስን በሌላ ጊዜ ከነበሩበት በታላቅ ... ከዚሁ ግርጌ የተለዋወጡትን ንግግር ስንመለከት ነው ፡፡

አፄ ዓምደ ጽዮን — ወዴት ነበርህ ?

አቡነ ፊልጶስ — መሬት በመላዋ የእግዚአብሔር ናት (ይኸውም ማለት የእግዚአብሔር አገር ሰፊ ስለሆነ ባንዱ አገር ነበርሁ) የሚለውን አልሰማህምን ?

አፄ ዓምደ ጽዮን — ምድር ለኔ ነው እንጂ ላንተ አልተሰጠህም ፡፡

አቡነ ፊልጶስ — ምድር የተፈጠረው ለሰው ልጅ ሁሉ ነው (3) ፡፡

ሆኖም የተከበሩትን እጨጌ በዚህ ዓይነት ማንገላታቱ ራሱ ጸጸቶት ይሁን ወይም መካረ ገብቶት ይሁን ወይም የእጨጌው መንገላታት በየአውራጃው በቤተ ክህነት ዘንድ ንቅናቄን ፈጥሮበት ይሁን አይታወቅም ንጉሡ ለእጨጌው ገንዘብ (ወርቅ) ልኮላቸው ኖሮ ባለፈው ውርደት ተቀይመው አልተቀበልም ብለው መልሰውም «ንጉሥ የላከልህን አልተቀበልም ብለህ መኩራትህ የምን በላውም የምትለብሰውም ሁሉ የንጉሡ መሆኑን አታውቅምን» ብሎ በቁጣ እንደመለሰላቸው የራሳቸው ገድል ያረጋግጣል (4) ፡፡

ገድሉን የጻፈው የቤተ ክህነት ሰው በመሆኑ ምናልባት በአጻጻፉ እጨጌውን የደገፈ ቢመስልም ዞሮ ዞሮ ይህን የመሰለው በሚገዛው አገር ላይ የሙሉ ባለቤት

(1) ገድለ ፊልጶስ ዘደብረ ሊባኖስ Turaiev-Secretariat du Corpus ... ገጽ 12 ፡፡
(2) ታሪክ ነገሥት ገጽ 32
(3) ምድረስ ወሀበ ለዕጓለ እመ ሕያው ፡ [illegible] 16 ፡፡
(4) ገድለ ፊልጶስ ምዕ. 20 ፡፡

ነት ስሜት የአፄ ዓምደ ጽዮን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነገሥታት እንደሆነ ሕዝቡም ይኸንኑ የነርሱን ስሜት አምኖ እንደሚቀበለው አይካድም ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ «በተቀባው ንጉሥ ላይ እጅህን አታንሣ ፤ የተቀባውን የረገመ ሞት ይገባዋል ። . . .» የሚል ጥቅስ በዋናው የብሉይ መጽሐፍ ይገኛል (1) የብሉይ መጽሐፍ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሳፍንት ነቢያትና ጻድቃን የጻፉትና ለሰው ልጅ መተዳደሪያ የተሰጠ ሕግ ነው ተብሎ የታመነ ነው ።

በኋለኛው ዘመን ፈረንሳዩ ሞንቴስኪዩ ስለ ሕግና ስለ አስተዳደር « Esprit de loï) በሚባለው መጽሐፉ አስተዳደር ሕግን በሚያወጣ ምክር ቤት ፤ ሕጉን በሚፈጽም የካቢኔ ባለሥልጣን ፤ ሕጉ ሲዛባ በሚፈርድ የዳኝነት ድርጅት ይመራ ያለው አዲስ አሳብ በዚያን ዘመን እንኳን በኢትዮጵያ በራሱም በፈረንሳዊ አገር ቢሆን አሳቡም ንቅናቄውም ገና አልተጸነሰም ።

ንጉሥ በጣም ከመከበሩና ከመፈራቱ የተነሣ ከፉኛ ቅጣት በሰው አካል ላይ በፈረደ ጊዜ አንዱን ጥፋተኛ በመግደል ፈንታ ዓይኑ ጠፍቶ ይታሠር እግሩ ተቆርጦ ይጋዝ ብሎ በፈረደ ጊዜ እንኳን እንደ ርኅሩኅ ይቆጠራል (2) ።

ስለዚህ ከሰሎሞን ዘር የተወለደው ሚሮን ተቀብቶ የነገሠው ከዙፋን ከወጣ በኋላ የፈቀደውን ቢያደርግ እግዚአብሔር በርሱ ተመስሎ እንዳደረገው ስለሚቆጠር ከዚህ ውጭ ሌላ የመቃወም አሳብ የሚያመነጭ ቢገኝ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በቀጥታ እንደተቃወመ ይቆጠራል ።

ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ጸሐፌ ትእዛዙ አዛዥ ተክለ ሥላሴ (ጢኖ) «በዓለሙ (በግዛቱ) ንጉሥ የእግዚአብሔር አምሳል ስለሆነ የፈቀደውን ያከብራል በጠላው ላይ መከራ ማምጣትና ማደኅየት ይችላል» ብሎ ባዘጋጀው በሱስንዮስ ዜና መዋዕል ላይ ጽፎአል (3) ። ከርሱ በኋላ የዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድን ታሪክ የጻፈው አዛዥ ሐዋርያ ክርስቶስ «የንጉሥ ትእዛዝ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው የንጉሥን ትእዛዝ የሰማ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደ ሰማ ይቆጠራል» ብሏል (4) ።

የነገሥታት ሁሉ ጠባይ እንደማናቸውም ሰው አንድ አይደለም ። ባንድ የአስተያየት መሥመርም አይመራም ። ሰውን መድፈር ማጉላላት የማይወድ ቅንንና ትክክለኛ ፍርድ መፍረድ ደስ የሚለው የሰው ገንዘብ የሕዝብ ሀብት መንካት ደስ የማይለው በገናናው ሥልጣኑ የማይጠቀም በፍጥረቱ መንፈሳዊ ለሕዝብና ላገር አገልግሎት መውጣት መውረድ ደስ የሚለው ንጉሥ አለ ።

በ፲፫፻፸፩ ዓ. ም. የነገሠው ግማደ መስቀልን ከኢየሩሳሌም ያስመጣው ዓፄ

(1) አንደኛ ሳሙኤል ምዕ. 26 ቍ. 9 ሁለተኛ ሳሙኤል ምዕ. 19 - 21
(2) Annale regum Iyasu II et Iyoas-Guidi-Corpusco pg 81. Annales Yohanhes I Iyasu Ier Bekaffa-Guidi Corpusco ምዕ. 45 ገጽ 158 ።
(3) Chronica de Susenyos ገጽ 280 - 300 ።
(4) Annale Johannesl et Bekaffa-Guidi ገጽ 162 ።

ዳዊት ፤ በ፲፬፻፲፬ ዓ.ም. የነገሠው ልጁ ቴዎድሮስ እንደ ጕንደሩ ንጉሥ እንደ ጻድቁ ዮሐንስ ጽድቃቸውና ትሩፋታቸው ይወራል ። ቴዎድሮስ የራሱን ሀብት እያወጣ ለሕዝብ የሚያድልና ባንድ ሚስት የተወሰነ ጻድቅ እንደነበረ ከስንክሳር ላይ ይገኛል (1) ። ምንጩ አይታወቅም እንጂ የሕዝብ ገንዘብ አልነካም በማለት ለግሉ መተዳደሪያ ሰሌን እየሰፋ በዘፆ ሽያጭ ይኖር ነበር የሚሉ አሉ ።

እኔ ሳልሞት ልጅሽን ለማንገሥ ከመነኮሳት ተላልከሻል በማለት ሚስታቸውን እስከ መግረፍ የደረሱት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በየአውራጃው ቤት ልጆቻቸውንና የቅርብ ዘመዶቻቸውን በመሾም ሙሉ የቤተ ክህነትንና የቤተ መንግሥትን ሥልጣን በእጃቸው ጠቅለው ሥራውን በወኪል ብቻ ያሠሩትን ልጃቸው በእደ ማርያም በዘመናቸው ይህ ዓይነት አገዛዝ እያዋጣም በማለት ከታላላቆቹ ባለሥልጣኖች ለርሳቸው የሚታመኑትን እየመረጡ በማዕርግ ስም በሽልማት እያሳደጉ በየአውራጃው ሾመዋል (2) ። ስለዚህ እንደ ማናቸውም ሰው የነገሥታት አሳብና ጠባይ ሁሉ ይለያያል ።

በዚህ መካከል የምንመለከተው ሕዝቡ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ያለውን ጽኑ ፍቅር ነው ። ባገሪቱ የገባውና ተስፋፍቶ የተመሠረተው በዳዊትና በሰሎሞን ንጉሣዊ አገዛዝ የመተዳደር ትምህርት ስለሆነ ከዚያ ውጭ አንድ አገር ያለ ንጉሥ ይተዳደራል ብሎ ሕዝቡ አያምንም ። የግሪኮችን የሮማውያንን የሬፐብሊክ አስተዳደር መኖሩን ዩልዮስ ቄሣር [illegible]ሬፐብሊኩን አገዛዝ ወደ ንጉሣዊ አገዛዝ ሊለውጥ አስቦ ነው ፤ ገዳዩ ብሩቱስ የሬፐብሊክ አስተዳደር ፍቅር ያደረበት ነው የሚለው የውጭ አገር የታሪክ ዝና ባገራችን በዚያን ሰዓት የሰማ መኖሩ ያጠራጥራል ። የሰማ ቢኖርም በከሃዲነት እንዳይጠረጠርና አደጋ እንዳይደርስበት ላለማውራት መጠንቀቅ አለበት ።

ንጉሠ ነገሥቱ የዳዊት ዘር ከእግዚአብሔር የተቀባ የአምላክ እንደራሴ በመሆኑ እንዳይታይም በቤትም በጉዞም በመጋረጃ እየተከለለ ስለሚኖር በሕዝብ ዘንድ እንደ አንድ ብርቅና ድንቅ ፍጡር ሆኖ ነው የሚታየው (3) ። በ፲ኛው መቶ ዓ.ም. ላይ አይዙር የሚባል ንጉሥ በነገሠበት ቀን በዓለ ንግሡን ለማክበር የተሰበሰበው የከተማ ሕዝብ እሰቲ እንየው በማለት በመዳሰስና በመጨበጥ እስጨንቆ እንደገደለውና ከዚያ ወዲህ በንጉሥ ፊት የከልከላ ሥራ እንደጸና ለማመልከት ደንበኛው ታሪከ ነገሥት እንደዚህ ይላል «ለግማሽ ቀን የነገሠው አይዙር የከተማው ሰው ሁሉ እየተረባረበ እጅ ሲነሣው ከጭንቅ ብዛት የተነሣ ሞተ ፤ እንዲሁም ብዙ ሰዎች ሞቱ ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከንጉሥ ፊት የመቆም ከልከላ ተጀመረ» (4) ።

(1) ስንክሳር ሰኔ 29 ቀን

(2) የኢ.ት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 31. ገጽ 40 - 44

(3) Verdadeira informacao = Alvarez ምዕ. 93

(4) ዐ. . ለአይዙር ዘንግሠ መንፈቀ ዕለት ወሞተ በጭንቅ እንዘ ይነሥእዎ እደ ዙሉ ሰብአ ከተማ ወሞቱ ብዙኃን ሰብእ ምስሌሁ እሚሃ ተወጥነ አጽንዖ ከልከላ እምገጸ ንጉሥ» ታሪክ ነገ. ገጽ 31 ።

በንጉሠ ነገሥትነት በሚኖርበት ዘመን ነጋሢው ቀጸላውን ተገልጦ እንደልቡ ተዝናንቶ ከቤተ ሰቡ ወይም ከቅርብ ባለሥልጣኑ ከዓቃቤ ሰዓቱና ከቢትወደዱ ጋር ይነጋገር ይጫወት እንደሆን ነው እንጂ እንደዛሬ ንጉሠ ነገሥት ያለ ሽፋን ያለ መጋረጃ ወደ ውጭ እየወጣ ፊት ለፊት አቤቱታ እየሰማ ራሱ በቀጥታ ሰውን ማነጋገር አይችልም ። የውጭ አገር ሰው ቢመጣም በቶሎ ተቀብሎ ፊት ለፊት አነጋግሮ ያገርን ጉዳይ በመፈጸም ፈንታ እንግዳ ከውጭ አገር በመጣ ጊዜ ያለ ደጅ ጥናት እንደማይቀበለው ሲቀበለውም የሚያነጋግረው በ፫ኛ ሰው (ዓቃቤ ሰዓት) አማካይነት መሆኑን ወደፊት በፖርቱጋሎቹ ጉብኝት ምዕራፍ ላይ እናነባለን ።

ይኸም የክብርና የሥነ ሥርዓት የልማድ ብዛት በበኩሉ ለኢትዮጵያ አለመሠልጠን ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አብሮ የሚቆጠር ነው ። ነገር ግን ይህ የግርዶሽ ልምድ መጠኑ ከግራኝ ወረራ በኋላ በጐንደር ዘመነ መንግሥት የቀረ ወይም የተቀነሰ ይመስላል ።

## ምዕራፍ ፫

## የዘመኑ መንፈሳዊ ትምህርትና ከሥልጣኔ ጋር ያለው መራራቅ

በዚህ በመካከለኛው ዘመን የነበሩት ነገሥታ[illegible]ሕዝቡ የአክሱም ሥልጣኔ አመለጣቸው እንጂ ከአክሱም ወርሰው የሚመሩበት ብዙ የሥልጣኔ የወግና የስነ ሥርዓት ቅርስ እንደያዙ ናቸው ። ከዚህም ትምህርት ዋና መሣሪያ የሆነውና ከአክሱም ወርሰው የሚጠቀሙበት ፊደልና ለዚያ ዘመን በቂ ሆኖ ሊገመት የሚችል ስነ ጽሑፍ አለ ።

አክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባ ፣ በግሪክ ፣ በግዕዝ ፊደል የተጻፉ የነገሥታቱን ጀብዱ የሚተርኩ ጽሑፎች ሲታዩ ከ፫ቱ ግሪኩ እንደዛሬው እንግሊዝኛ ግሪኮች ከገነኑበት ከታላቁ እስክንድር ወዲህ በመካከለኛው ምሥራቅ እንደተመሠረተ በዚያው ይዞታ ወደ ኢትዮጵያ የዘለቀ ዓለም አቀፍ መገናኛ በመሆኑ እንጂ ባዕድነቱ የማይጠረጠር ነው ። ስለዚህ ያገር ፊደሎች ተብለው ሊቆጠሩ የሚገባቸው የፊተኛው የሳባውና የኋለኛው የግዕዙ ፊደሎችና በነርሱ የተጻፉት ጽሑፎች ናቸው ።

የአክሱምን መንግሥት የመሠረቱት ከደቡብ ዓረብ የመጡ የሴም ነገድ መሆናቸውን ስማቸውም በየቅርንጫፋቸው ሳባ ፡ ሀበሳን ፡ ሂማያሪት ፣ ሆሜሪት እንደሚባሉ ብዙ ጊዜ ተጽፏል ። የሳባ ፊደል የሳባዎች መሆኑ ሲታወቅ በሳባ ፊደል የቀሩት በሴማዊነት ከሳባ የሚዛመዱት ሀበሳን ወይም ሂሚያሪት ይጠቀሙ ወይም እነርሱ ለብቻቸው የግዕዝ ባለቤት ይሁኑ አጣርቶ ማወቁ ይቸግራል ።

ስለዚህ የግዕዝ ፊደል በሳባ ፊደል ጐን ሲገኝ ራሱን ችሎ የመጣ መስሎ ባንድ ወገን ሲታይ በሌላ በኩል ደግሞ ከሳባው ፊደል የተወለደ መስሎ ይታያል ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ አራተኛው መቶ ዓመት ድረስ ሁለቱ ለየብቻ ሲኖሩ አናጋሪ የፊ

ዶል ምልክት አልነበራቸውም ነበር ። በኋላ ግን የሳባው ፊደል አቀማመጡ እየተለ ዋወጠ ግዕዝኛ ሆኖ በ፬ኛው መቶ ዓመት ላይ እናገሪ ምልክት ተበጅቶለት የግዕዙ ፊደል የሳባውን እያደር አጥፍቶ ከአክሱም መንግሥት ከ፬ኛው፥ ከ፭ኛው መቶ ዓ. ም. ወዲህ ብቻውን ባለቤት እየሆነ የዛጉዬዎችን ዘመን አሳልፎ እነዚ እስከ ጊዜያችን ደረሰ ።

እንግዲህ የታሪክ ፡ የስነ ጽሑፍ የትምህርት ሁሉ መሠረት ይህ የግዕዝ ፊደላ ችን ነው ። የትምህርቱ ጠቅላላ ኃላፊ ከላይ ከንጉሡ ንጉሠ ነገሥት ዝቅ ብሎ የቤተ ክህነ ቱና የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ናቸው ። ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ሲባ ልም ከሁለት በትክክል የተከፈለ የየአንዳንዱ ተግባር የተለየ ይመስላል እንጂ ከዚህ ይቱኖ አምላክ መንግሥት ከወሰደበት ከ፲፫ኛው ዓመት ዝቅ ብሎ በጐንደር ሁሉ የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱ ሥራና ተግባር ተያይዞም ተቀሕዶም ይኖ ራል ። ግብፃዊ ጳጳስ ኢትዮጵያዊ እጨጌ ቢኖሩም የቤተ መንግሥቱም የቤተ ክህነ ቱም የበላይ መሪ ንጉሡ ንጉሠ ነገሥቱ ነው ።

አንዱ የዚያን ዘመን ባለሥልጣን የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ሥራ ደርቦ ይሠራል ፡ ከሐድያው ገራድ ከዶዋሮው ገራድ ከባሌው ገራ ና ከዶፋቱ ጠላስማ በቀር የቀሩት የግራውና የቀኙ ቢትወደዶች የፈጠጋሩ ራስ የሸዋው ወይም የአማ ራው ጸሐፊ ላም ቅኔና ዜማ መጻሕፍት አዋቂዎች ይገኙባቸዋል ። ከገራዶቹ ውስጥ የማይገኙበት ምክንያት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንደሚታየው በነዚህ አገር ብዙ ጊዜ የሚሾሙት ያገር ባላባቶች እስላሞች በመሆናቸው ነው ። ነገር ግን ይኸንን የገራድነት (ገራዳነት) ሹመት በተለይ የባሌውንና የዶዋሮውን ከትግሬና ከአማራ መኳንንት ውስጥ አንዳንድ ስለሚሾሙት እነርሱም የተማሩ ሊሆኑ ይችላሉ ።

እንደዚሁም ነገሥታቱ ሳይቀር እንደ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፡ እንደ ዓፄ ናዖድ ያሉት በመንፈሳዊ ትምህርት የጠለቁ ቅኔና ዜማ የሚያውቁ አሉ ። ከጦር አለቆ ችም ውስጥ እንደዚሁ ምሑራን አሉባቸው ። ያፄ ገላውዴዎስ ዋና የጦር አለቃ አፈወ ድንግል የሚባለውን ታሪክ ነገሥቱ ባንድ ቦታ ላይ «ምሁር ካህን የተማ ረው ካህን» በሌላ ቦታ ላይ «ሊቀ ሠራዊት ጎሩያን ካህን ዓቢይ አፈወ ድንግል የምርጦች ሠራዊት አለቃ ትልቁ ካህን አፈወ ድንግል» ይለዋል ። ብዙዎቹ መኳን ንትና የጦር አለቆች የቤተ ክርስቲያን እልቅና በድርብ ይይዛሉ ። ራስ አፈወ ድን ግል በቤተ መንግሥት የሠራዊት የበላይ ሹም ሆኖ በቤተ ክህነት በክብር የተደባበ ማርያም አለቃ ነበር (1) ።

ለመንፈሳዊ ሥራ ተመድበው የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ ንቀው በብቸኝነት (ብሕትውና) የሚኖሩ የነዚያን የስመ ጥሩዎቹን የደብረ ዳሞን የደብረ ሐይቅን የደ ብረ ቢዘንን የዋልድባን ፡ የደብረ ሊባኖስን ገዳማት ኃላፊነት የያዙ አበምኔቶችና እጨጌዎች አሉ ። እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ ንጉሡ ለከፍተኛ ጉዳይ ካልጠራቸው ወይም ራሱ ወደ ነርሱ ካልሄደ በቀር በኑሮአቸው አብዛኛ ጊዜ ከመንግሥት የአስተ

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 106-107

ISIC

ዳደርና የጦርነት ሥልጣን የራቁ ናቸው ። ነገር ግን በሕልም ተገልጾልናል ፡ በራ እይ ዓይተናል ፤ ከጠላትህ ተዋጋ አትዋጋ ወይም ዛሬ ብትዋጋ ትሞታለህ ነገር ግን ትጸድቃለህ ፡ አድረህ ሰንብተህ ብትዋጋ ታሸንፋለህ ነገር ግን ትኰነናለህ በማለት በገዳማቸው የደወለ (የተማጠነ) ጥፉተኛ እንዳለ በማስማር በመፈራት ፡ በመከበር እንድ ከፍተኛ የሆነ የሩቅ መንፈሳዊ ሥልጣን አላቸው ። ነገር ግን የደብረ ሊባ ኖሱ መምህርና የደብረ ዳሞው ራቅ ሲሉ ለደብረ ሐይቁ መምህር ለአባ ኢየሱስ ሞዓ የተሰጠውን የዓቃቤ ሰዓትነትን የማዕርግ ስም የያዙት በደረጃ ከፍ ብለው የን ጉሡ ባለሟልና የቅርብ የንጉሡ የሥራ ረዳት መካሪው አማካሪው ሆነው ሲመሩ በየዜና መዋዕሉ ላይ ይታያል ።

አሁን በዚህ ምዕራፍ ላይ ልናመለከት የተነሣነው ስለትምህርት እንጂ ስለ ሹመት አይደለምና በጠቅላላው እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው የተማሩ ባለ ሥልጣኖች ትምህርታቸው ምንድነው በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ የሚሰጠው ጥና ትና ሊቅ የሚያሰኘው ትምህርት ምን ዓይነት ነው ብለን ማሰብ አለብን ። እንደው ነቱም ይኸን ለማወቅ ብዙ ማሰብና ብዙ መመራመር አስፈላጊ አይደለም ። ነጋሢ ዎቹ ከእሥራኤላውያን ዘር የወረዱ መሆናቸውን እንደተመለከትነው ብዙው ወግና ሥርዓት ሕጉም ከቋኤሎች ሕግ ጋር በብዛት ተያይዞ ይገኛል ።

ምንም እንኳን በክርስቲያናዊ መንገድ ታድሶ ቢሻሻል ሕጉና ወጉ ያው ከእሥ ራኤል ንጉሥ ከሰሎሞን ቤተ መንግሥት የመ[illegible]እንደመሆኑ መጠን ዋናውም የት ምህርታቸው መሠረት በተለይ የእሥራኤላውያን ታሪክ ያለበት ብሉይና ተተኩ የክርስትና መሠረት የሆነው የሐዲስ መጽሐፍ ነው ።

በዛሬው ዘመን ሳይቀር የትምህርት ሚኒስቴር እጅ ሳይገባበት በየገዳሙ ፡ በየ ደብሩ የሚሰጠው ከፊደል ቆጠራ እስከ ንባብ ፡ ከንባብ እስከ ድጓምት ፡ ከውዳሴ ማርያም ዜማ እስከ ድጓ ፤ ከቅኔ እስከ ሊቃውንተ መጻሕፍት ከብሉይ እስከ ሐዲስ ያለው ትምህርት በዚያን ጊዜ የሚሰጥ ትምህርትና ከዚያ ተያይዞ ጥንዳንዱ መንገድ ሁኔታውን እያሻሻለ እስከ ጊዜያችን የደረሰ ሁሉም የመንፈሳዊ ትምህርት ነው ።

## (1) ብሉይ ኪዳን

በግዕዝ ብሉይ ማለት ትርጓሜው በአማርኛ ያረጀ ወይም አሮጌ ማለት ነው ። ብሉይ ኪዳን አሮጌው የኪዳን ሕግ ያለበት ለማለት ነው ። አሮጌም ከመባል ያደረ ሰው ክርስቶስ በኋላ ከሰጠው አዲስ ሕግ በፊት የነበረ የመተዳደሪያ ሕግ "ሕገ ኦሪት" መሆኑን ለማመልከት ነው ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የዓለምና የአዳም የአፈጣጠሩና የተወላጁ ዝርዝር (ዘፍጥረት) ፤ እሥራኤሎች ከምድረ ግብፅ የወጡበት የመዝ መሪያውን ሕግ የተቀበ ሉበት ታሪክ (ዘፀዐት) ፤ ካህናቱ የሚተዳደሩበት ወይም ሕዝቡን በመንፈሳዊ ሥር ዓት የሚመሩት መሥዋዕት የሚያቀርቡበት የሚበላውና የማይበላው እንስሳ የተለየበት የወግና የሥነ ሥርዓት ደንብ የተሰጠበት (ዘሌዋውያን) ፤ የካህናቱና

የሕዝቡ ቍጥር እየተደለደለ በየተግባሩ የተመደበበት (ዘኍልቍ) ፣ የከነዓንን ምድር ሰጥቻችኋለሁና መሬቷን ስትይዙ የምትተዳደሩበት ብሎ በዝርዝር ድንጋጌ ሕግ የሰጠበት (ዘዳግም) ፣ ከዚያ በሙሴ ተከታይ በኢያሱ መሪነት ከነዓን (ፓለስቲን) ከገቡ በኋላ መዠመሪያ በመሳፍንቱ በነጌዴዎን በነሶምሶን በነሳሙኤል በነገሥታቱ በነሳዖል ፣ በነዳዊት ፣ በነሰሎሞን በሚተዳደሩበት ጊዜ ከዚሁ ከያዙት አገር የልዩ ልዩ ነገድ ሕዝብ (ፍልስጥኤማውያን አሞናውያን አጋራውያን) ጋር በየጊዜው የተዋጉበት የጦርነት ታሪክ ከዚያ ደግሞ ከሰሎሞን ሞት በኋላ መንግሥቱ ከሁለት ተከፍሎ የሰሜኑ አሥሩ ነገድ ያሉበት የእሥራኤል መንግሥት የደቡቡ ክፍል (የይሁዳና የብንያም) የይሁዳ መንግሥት ተብሎ እንደቆየ የደቡቡን የባቢሎን መንግሥት የሰሜኑን የአሦር ነገሥታት አፈራርሰው ሕዝቡን ማርከው የወሰዱበት ሰሎሞን ያሠራው ስመ ጥሩው ቤተ መቅደስ በባቢሎኖቹ የፈረሰበት ቀጥሎ ባቢሎን በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ኃይል ሲወድቅ በዚሁ ንጉሥ ፈቃድ ምርኮኞቹ እሥራኤሎች ከባቢሎን ተመልሰው እነዘሩባቤል እነነህምያ ከተማቸውን አድሰው እንደገና በመቋቋም ያንሰራሩበት በዝርዝር ተጽፏል ፡ እርሱም ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ መጽሐፈ አስቴር ያለው ነው ።

ከነዚህ መጻሕፍት ጋር ኢዮብ ከወረደበት መከራ የታገሠበት ንጉሡ ዳዊት ጠላቱን ጣልልኝ ከጠላቴ ጠብቀኝ እያለ በእግረ እስካከ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር መዝሙር የገጠመበት ከ፻፶፩ ልጁ የሰሎሞን ብዙ የምሳሌ ምክርና ፍልስፍና ያለበት ድርሰት ለሚስቱ ከደረሰው የፍቅር ግጥም ጋር (ምሳሌ መክብብ መኃልየ መኃልይ)-ከዚያ ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ድረስ በየጊዜው የተነሡት ታላላቅና ትናናሽ ነቢያት (1) ከአምላካችሁ ሕግና ሥርዓት አትራቁ በዙሪያችሁ የሚገኘውን ጣዖት አታምልኩ ብታመልኩ ትጠፋላችሁ በማለት ነገሥታቱን ሕዝቡን የመከሩበት በጎ ተግባር (ሞራል) ያስተማሩበት ስለመጪው ሁኔታ የተነበዩት ይገኛል ።

## (2) ሐዲስ ኪዳን

እሥራኤላውያን የአብርሃም ልጆች የእግዚአብሔር ምርጥ ቢባሉም በእግዚአብሔር አምልኮ ቀደምት ቢሆኑም ነቢያት ቢናገሯቸውም ከተገዥነት አልዳኑም ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፲፫ኛው (2) መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በሙሴ መሪነት እላይ እንዳመለከትነው ከግብፅ ወጥተው በከነዓን (የዛሬው እሥራኤል ወይም ፓለስቲን) ከተመሠረቱና በ፮ኛውና በ፯ኛው መቶ ዓመት ላይ በአሦርና በባቢሎን መንግሥታቸው ከፈራረሰ በኋላ በፋርሶች ዘመን በዕዝራና በነህምያ መሪነት (፫፻፺፰ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) መቋቋም እንደ ዠመሩ የፋርስን መንግሥት የደመሰሰው ትልቁ እስክንድር ያዛቸው ። የርሱ የጦር አሊቃ እንቶያ

(1) በግዕዝ ዓበይተ ነቢያት ደቂቀ ነቢያት ያላቸዋል

(2) የዘመኑ ቍጥር ሁልጊዜ አከራካሪ ነው

ቆስ ፬ኛ (፻፸፭ - ፻፷፬ ዓመት) ሲያስተዳድራቸው ለግሪክ አማልክት እንሰግድም በማለት በስምዖን መቃቢ መሪነት ሸፍተው ብዙ መጉላላት ደረሰባቸው ። ከግሪክ አገዛዝ በኋላም ሮማውያን ዓለምን ሲወሩ ለሮማውያን አንገዛም ብለው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሰባ ዓመት በጢጦስ (ቲቱስ) መሪነት የደረሰባቸው ሥቃይና ስደት በታሪክ የታወቀ ነው (1) ።

እንግዲህ ከግሪክ አገዛዝ ወደ ሮማውያን በተዛወሩበት ጊዜ በአውግስጦስ ቄሣር ዘመን ክርስቶስ ከይሁዳ ነገድና ከዳዊት ከምትወለደው ከማርያም በቤተ ልሔም ተወልዶ ፴ ዓመት ከሞላው በኋላ ክርስትናን እየዞረ አስተማረ ። የርሱ አዲስ ትምህርት ከአስተዳዳሪዎቹ ከሮማውያን ሃይማኖት የራቀ ከሙሴ የኦሪት ሕግ ጋር የሚለያይ አዲስ አስተያየት የሞላበት የሰውን እኩልነት ርኅራኄን ይቅርታን ፍቅርን የያዘ ስለሆነ ራሱንም የእግዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በዚሁ ለክብራቸውና ለቀድሞው የኦሪት ሕግና ትምህርት ቀናተኛ የሆኑት የአይሁድ ጸሐፊዎችና ባለሕጎች (ጸሐፍት ፈሪሳውያን) ይዘው አሠሩት ። ራሳቸው በፈቃዳቸው ለማሠርም ለመግደልም መብት ስለሌላቸው ላስተዳዳሪው ለጲላጦስ አሥረው አቀረቡት ። ጲላጦስ ነገሩን መርምሮ እንደተረዳው የክሱ ምክንያት ፩ኛ በቅንዓት ፪ኛ በርስ በርስ የሃይማኖት ክርክር መሆኑን በመረዳት ሊተወው ፈልጎ ነበር ።

ዳሩ ግን ራሱን የእግዚአብሔር ልጅና የአይሁድ ንጉሥ ሲያደርግ እኛ ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም ስንል ብትተው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ብለው ስለአስፈራሩት በልቡ ያልፈቀደውን ፍርድ ከጌታው ብቻ ላለመጣላት ከደሙ ንጹሕ መሆኑን ለማስረዳት እጁን ባደባባይ ታጥቦ እንደሰጣቸውና እንደገደሉት ከተቀበረም በኋላ በ፫ኛው ቀን እንደተነሣ በተነሣም በ፵ኛው ቀን ወደ ሰማይ እንደወጣ በአራቱ ወንጌላውያን እጅ የተጻፈው ምስክር ነው ።

ስለዚህ ይህን አዲስ የክርስቶስን ትምህርት ከርሱ ጋር የነበሩት ማቴዎስ ፣ ሉቃስ ፣ ዮሐንስ ያልነበረው ማርቆስ ከጴጥሮስና ከነበሩ እየጠየቀ በአራት መጽሐፍ ላይ ጽፈው አስተማሩ ። ይኸንኑ ትምህርት ጳውሎስ ከቀድሞው ከኦሪቱ ትምህርት ጋር እያገናዘበ በማስተማር ለሮማውያን በዚያን ዘመን ለገነኑት ለግሪክ የከተማ ነዋሪዎች (ለቆሮንቶስ ለገላትያ ፣ ለኤፌሶን ፣ ለፊልጵስዩስ ፣ ለቆላስይስ ፣ ለተሰሎንቄ . . . . .) ለዕብራውያንም መልእክት እየጻፈ የአስተማረበት ከያዕቆብና ከጴጥሮስ ከዮሐንስና ከይሁዳ መልእክቶች ጋር የዮሐንስ ራዕይ ተጨምሮ አዲሱን ትምህርት የሚያስረዳ መጽሐፍ ሆነ ። በዚህ ምክንያትም ስሙ ሐዲስ ኪዳን ተባለ።

## (3) የሊቃውንት መጻሕፍት

የላይኛውን የሐዲስ ትምህርት ክርስቶስ ከመሠረተው ሐዋርያት ከአስፋፉት በኋላ በሚቀጥለው ጊዜ በታላላቆቹ ከተሞች በቂሣርያ ፣ በቍስጥንጥንያ ፣ በእስክንድ

(1) Histoire ancienne des juifs-la guerre des juifs...Flavius Josephe-Livres V-VIII.

ርያ ፤ በእንጾኪያ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እየተነሡ በብሉይና በሐዲስ መሠረት ከአእምሮአቸውም እየመነጩ አዳዲስ መጻሕፍ በዝርዝር እየጻፉ ክርስትናን አስፋፉ ። ከነዚህም ስመ ጥሩዎቹ አባ አውሳብዮስ የቂሳርያ ኤጲስ ቆጶስ (፪፻፷፫ - ፫፻፴፱) አባ ቄርሎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት (፫፻፸፮ - ፬፻፵፬) ዮሐንስ አፈወርቅ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት (፫፻፵፯ - ፬፻፯) የደረሱት ድርሰት ስማቸውን ሲያስጠራው ይኖራል ። ደግሞ ከዚሁ ጋር ተጠራቅሞ የተደረጀ እንደ ሃይማኖተ አበው እንደ መጽሐፈ ሐዊ ያለው ይገኛል ።

በክርስቶስ ባሕርይ ምክንያት ከ፭ኛው መቶ ዓ. ም. ወዲህ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከቍስጥንጥንያና ከሮማ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ ለብቻዋ በራሷ የእምነት መንገድ ትምህርቷን ስታስፋፋ የሮማና የቁስጥንጥንያ ታላላቅ ሊቃነ ጳጳሳትም በየመንገዳቸው የክርስትናን ትምህርት አስፋፉ ። የሁሉም የትምህርት ልዩነት ወደፊት በአፄ ገላውዴዎስ ዘመን ተጽፎ ይገኛል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ሊቃውንት ከልጅነታቸው ጀምረው በትጋት እየተማሩ የሚያድጉት ከእድገት በኋላ ምሁራን ወይም ሊቃውንት ተብለው የሚመሰገኑበትና የሚከበሩበት እነዚህ ከዚህ በላይ በሦስት ታላላቅ መደብ የተከፈሉት የብሉይ ፣ የሐዲስ ፣ የሊቃውንት ትምህርት ናቸው ።

ከነርሱም ጋር ምንናን ፣ ብሕትውናን ፣ ምንኩስናን የሚያወድሰው ዮሐንስ ሳባ የተባለው ያዘጋጀው ፀኛ አረጋዊ መንፈሳዊ የሚባለው የነነዌው ተወላጅ ይስሐቅ ያዘጋጀው ማር ይስሐቅ ተብሎ በስሙ የሚጠራው ከፊልክስዩስ ጋር ከሌሎችም ጥቃቅን ጽሑፍ ወይም ከዓረብኛና ከግሪክ የተተረጐሙ የሰማዕታትና የጻድቃን ገድል በያይነቱ በየዘመኑ ተጨማምሮበታል ። እነዚህንም የወደደ በሐዲስና በብሉይ ትምህርቱ ላይ ለሊቅነት ብቻ ሳይሆን ለጽድቅና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጭምር ይጠቀምባቸዋል ።

ለየክብረ በዓሉ የሚዜመው በያይነቱ መስተጋብእ እርያም ክስተት ምዕራፍ ድጓ ጾመ ድጓ የሚባለው ሁሉ የተዘጋጀው ከዚሁ ከብሉይና ከሐዲስ ከሊቃውንት እየተመጣጣ ነው ። ሊቃውንቱ እነዚህን መጻሕፍትና የሰማዕቱን ፣ የጻድቃኑን ወይም የመላእክቱን ገድልና ድርሳን እያስማሙ ለዕለትና ላመት የሚሆነውን ዜማ መድበዋል ።

ለበዓል ቀን ለነዚሁ ጻድቃንና ሰማዕታት ክብር ከሁኑ ሰምና ወርቅ እያደረገ ቤት እየመታ አስቀድሞ ብቻውን አሰላስሎ የሚደርሰውና በኋላ በቤተ ክርስቲያንና በቤተ መንግሥት የሚናገረው የቅኔ ግዕዝኛ ግተም ምንም እንኳን የቅኔው ፈጣሪ ከሀኑ ቢሆን ለአገጣጠሙ መሠረት ማድረግ ያለበት ብሉይና ሐዲስን ነው ይኸም ቅኔ እንደዜማው ቅኔው ከሚደረስላቸው የጻድቃንና የሰማዕታት የመላእክት የሕይወት ታሪክ ጋር መያያዝ አለበት ።

ለምሳሌ ጥር ፲፩ ቀን የጥምቀት በዓል እንዲሆን ተወስኗል ። ከዋዜማው ከጥር ፲ ቀን ጀምሮ ሌሊቱን ጭምር በ፲፪ ቀን ታቦታቱ ወጥተው እስኪገቡ ድረስ የክርስቶስ ከማርያም ተወልዶ በአካል ለሰው ልጅ መገለጡ ሰው ሆኖ በዮርዳኖስ መጠ

መቁ በተጠመቀበት ጊዜ «ይህ ነው ልጄ ርሱን ስሙት የሚል የአብ ቃል ከደመና መሰማቱ» እየተጠቀሰ እንደሚዜም ባለቅኔም ለዚህ ዕለት ተስማሚ ቅኔ ገጣጥሞ የሚያቀርበው ከዚህ ታሪካዊ መስመር ሳይወጣ ነው ።

(4) ሥጋዊ ዕውቀት

ይኸን ከዚህ በላይ የተመለከተውን መንፈሳዊ ትምህርት አጋማሹን ይሁን ሙሉውን ለሊቃውንትነት የታደሉት እንደ ችሎታቸው ይማራሉ ። በሁሉ ሊቅ ለመሆን ከብዛቱ የተነሣ ስለሚያስቸግር አንዳንዱ ሊቅ ሁሉንም በመጠኑ ካደረሰ በኋላ ባንዱ ክፍል ተመርቆ የብሉይ ሊቅ ፡ የሐዲስ ሊቅ ፡ የሊቃውንት መጽሐፍ ሊቅ የዜማ መምህር የሰዋስውና የቅኔ መምህር ይሆናል ። የቻለም የብሉይና የሐዲስ ሊቅ ሆኖ ዜማ የሚያስተምር ቅኔ የሚነግር ሞልቷል ።

ደግሞ አንዳንዶቹ ችሎታቸው የፈቀደላቸው ከዚህ ከመንፈሳዊው ትምህርት ወጣ እያሉ ከግሪክ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመውን እንደ ዮሐንስ መደብር ያለውን የዓለም ታሪክ እንደ ዜና እስክንድር ያለውን የታሪክ መጽሐፍ እንደ ጠቢበ ጠቢባን ያለውን የፍልስፍና ጽሑፍ እንደ አቡሻክር ያለውን የጊዜና የዘመን መለያ እንደ ክብረ ነገሥትና እንደ ታሪከ ነገሥት እንደ ሥርዓተ መንግሥት የመሳሰለውን በመንፈሳዊ ትምህርታቸው ላይ ፲፱፻ዊ ትምህርት የሚጨምሩ በብርቅ ይገኛሉ ።

ብርቅ የሚሆንበት ምክንያት መጽሐፉ ራሱ የሚገኘው በብርቅ በቤተ መንግሥትና ወይም በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ ስለሆነ ነው ። መንፈሳዊው ትምህርት እንደልብ ሲገኝ ይኸን ሥጋዊና ታሪክ ነክ የሆነውን የሚያውቀው መጠነኛ እንደመሆኑ መጠን ትምህርቱም የለም ። አዋቂውም ሌላው አውቆ ርሱ እንዳይረክስ ዕውቀቱን ለራሱ ጨብጦ እንዲከበርበት ስለሚፈልግ እምብዛም ማስተማር አይወድም ። ሲያስተምርም እየቆጠበ በብርቅ ለወዳጁና ለልጁ ነው ።

ስለዚህ መደምደሚያውን በኢትዮጵያ ከ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ከፊደል ቆጠራ በኋላ የሚሰጠው ትምህርት ሁሉ መንፈሳዊ ነው ማለት ነው ፡ ሥጋዊ ፍልስፍና ቢኖርበትም አብዛኛው ጊዜ ከነዚያው እላይ ካመለከትናቸው ከብሉይና ከሐዲስ ፤ ከሊቃውንት ወይም ከሰማዕታት ገድልና ድርሳን ወይም ለነርሱ ከተገጠመው የመልክ ግጥም መውጣት የለበትም ።

በኢትዮጵያ ትምህርት ቤት የግሪኮቹ ሊቃውንት የነሖሜር ፣ የነሶክራት ፡ የነፕላቶን ፤ የነአሪስቶት ያስተዳደርና የፍልስፍና ትምህርታቸው በቁም ነገር ተወስዶ እንደ ብሉይና እንደ ሐዲስ መደብ ተሰጥቶት ትምህርት አይሰጥበትም ። ሚካኤል ኤጲስ ቆጶስ የሚባለው ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጐመው መጽሐፈ ፈላስፋ ጠቢባን የነዚሁ የግሪኮች ፍልስፍና ቢኖርበትም የዚህ መጽሐፍ አንባቢና አዋቂ እላይ እንዳልሁት ብርቅ ነው ።

ከዚሁ ውጭ የአውሮፓ ሕዝብ ግን ከብሉይና ከሐዲስ ትምህርት አልፎ በዚሁ ዘመን ለማስፋፋት የሚታገልበት የሕክምና፣ የመሐንዲስነት የቢትና የመንገድ አሠራር የጽንዐ ትርጉም የብረታ ብረት የባሩድ አሠራር ፈጠራ ችሎታ ተብሎ የባለሙ ለሚናቸው እሳብ በነቸረው ዕውቀትና በመንፈሳዊው ትምህርት ብቻ እንደታሠረ ኖረ ።

አባቶቻችን ዕውቀትም ትጋትም የአካልና የመንፈስ ብርታትም እያላቸው ይኸን ጠቃሚ የሆነውን የዘመኑን ለየ ለየ ዕውቀት መገፋ እቅርቦው ሳይሆን እውቀው በጋተት የተጫት ይመስላል ። ምክንያቱም እነዚኛው ይህ ሁሉ እላይ ያመለከትነው ለየ ለየ የኪሊበኛ የመሐንዲስነት የሕክምና ወይም የብረታብረት ሥራ የመነጨው ከተመረጠው ሕዝብ ከእምሬ ኢል ሳይሆን ከእምሬ ኢል ከማይወለዱ ከአሕዛብ ከፈረንጆች የተገኘ ነው ብለው ይሆናል ። በዚህም ላይ እውሉስ በመልእክቱ እኛ ከቤተ ማርያናችሁ ለሌ መልእክ እንኳ መጥቶ በያስተምራችሁ እንዳትቀበሉ ብሎ ያወዘውን ለዚህኛው ለመጋዋው ትምህርት እንዲውል አድርገውት እንደሆን እይታወቅም (1) ።

ያንም የዚሀ የሥልጣኔ ባለቤቶች ፈረንጆች ግማሾቹ እንደ ፖርቱጋል እንደ ኢጣልያን እንደ ፈረንሳዮች ያሉት ከርስቶስ ቀ ባሕርይ እለው የሚሉ ግማሾቹ እንደ እንግሊዞች እንደ ጀርመን ... ማርያም አትማልድም የሚሉ ስለ እሉ እነርሱም ዓርብ ሮብ አይጾሙም በአሬት መሉ ቢሊከለውን የእነግ ሥጋ ይበላሉ ሲባል ከነዚሁ ጋር መቀራረብ ከነዚሁ መምህራን ትምህርት መቀበል ይቀፋቸዋል ። እነዚህን ከመሰሉ እረማውያን የሚገኘውን ትምህርት ከመቀበል አለመቀበልን የሚመርጡ ይመስላል ።

የያማኖታችንና የእማኛን ጉዳይ በትምህርት ከማነኛው ጋራ ጋር ለያቶ መረዳት ለበ ያን ገዚ ለአለምና እስተያየት [illegible] ።

እያያረ የእስላሞችን እያንቸነት እርስ [illegible] እንደምንነበው በግድ ከፖርቱጋሎች ግንኙነት [illegible] ከፈረንጆች ሥልጣኔ ዕውቀት ለመረት እላፎ [illegible] ዘመን እስተያ የት በቁ የሆኑና የባለ [illegible] ባሕርይ ይከፍላሉ ። [illegible] ለእ ከፈረንጆች እየቀረ ችና ፈላስፎች ውስጥ [illegible] በለ ማድ የተቀበለነውን [illegible] እለብን ብሏል ። በፕሮቶ የሚ [illegible] እምላክ ነው ([illegible]) እንደ ከግሪክ የተሰየ ለብዙ [illegible] (Demiurge) የሰየሙ [illegible] የሚባል ፈጣሪ እንደ [illegible] በተሰማ

ቍጥር ነገሩ እየሰቀጠጠ በቀድሞው ጥላቻ ላይ አዲስ ጥላቻ እንደሚጨምር ግልጽ ነው ።

ይኸም እንኳን በኢትዮጵያና በዚያው በአውሮፓም ቢሆን የኋላ የሕዝብና የሊቆች እንቅስቃሴ (Revolution) እያደር እስኪደመስሰው ድረስ ይኸን የመሳሰለውን አሳብ አልፈው አልፈው ያፈለቁ ሰዎች በጳጳሳትና በነገሥታት ሥልጣን እየተያዙ ሲታሠሩም ሲገረፉም ኖረዋል ።

በትርባችን ያሉት በዘርና በልማድ የሚቀርቡን ዓረቦችና ቱርኮች ዕውቀታቸው ከአውሮፖች ዝቅ ቢልም ለጊዜውና ላለንበት ደረጃ በቂ የሆነ ዕውቀት አላቸው ። የቀረው ቢቀር የባሩድ ሥራ ይችላሉ ። ነገር ግን እነርሱ ደግሞ ክርስቶስ አምላክ አይደለም አምላክም አይወለድም ስለሚሉ ግንኙነቱና ትምህርቱ ከፈረንጆቹ ጋር እንጻቃተ ከነዚህም ጋር ተማሪና አስተማሪ ሆኖ አብሮ ውሎ አድሮ በማኅበራዊ ኑሮ ተባብሮ ትምህርት የመቅሰሙ ነገር በቤተ ክህነቱም በቤተ መንግሥቱም ዘንድ አዳጋች ሆኖ ኖረ ። የፈረንጆቹን ሥልጣኔያቸውን ፣ ዕውቀታቸውን ሀብታቸውን ቢረዱትም «ምን ይደረግ ሀብት ጉትነት ዕውቀት ለአሕዛብ ተሰጠ ፣ ዘመን ያመጣው ነው ፏኛው ሺ የወለደው ነው» እያሉ የነዚያን ሥልጣኔ ከመናቅ በነርሱ አለመስልጠን ከመጽናናት በቀር አዲስ የሥልጣኔ በር ሊከፍት የሚደፍር አልተገኘም ። ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ በኑሮ በልማድ የተሳሠረ በእምነት በአሳብ የተዋሐደ ስለሆነ ሁሉም የቆየውን ል፪ዩና ሥርዓት ላለማስደፈር ሲል የተያዘውን ነዋሪ ዕውቀት በቂ አድርጎ በመመልከት ለመከላከያ መድን ለሆነው ለብረታ ብረትና ለባሩድ ሥራ በጠቅላላው ለሥልጣኔ ፊቱን አዙሮ ዠርባውን በሰጠበት ዘመን ሳይታሰብ የግራኝ አህመድ ወረራ እንደ ጐርፍ ደርሶ ሁሉንም እንዳጥለቀለቀው ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

የጦሩ መከራ በየአለበት እያጥለቀለቀ ፋታ በነሣበት ሰዓት የተቀቡት ንጉሠ ነገሥት ታላላቆቹ ራሶችና ቢትወደዶች ፣ ዓቃቤ ሰዓቶችና ባሕር ነጋሾች የበዛውን ወግና ሥነ ሥርዓት ክብራቸውን ወደጐን ችላ ብለው ባጭር ታጥቀው ከባሕር ማዶ መምህራን እየቀጠሩ በጦር ትምህርት ጠንክረው አለመሠልጠናቸው የሰይፍ አመታት የጋሻ አመካከት በትጋት አለመማራቸው እንደሚቆጫቸው የታወቀ ነው ።

ይኸንን ሁሉ እናውቃለን ቢሉም ለመከላከያና ጠላትን ለማጥቃያ ደንበኛ መድን የሆነውን የዘመኑን የጦር መሣሪያ በባሩድ የሚተኰስ መድፍና ነፍጥ ሳያሰናዱ መቅረታቸው እንደሚጸጽታቸው እርግጥ ነው ። ኋላ ግን ያለፈው የሰላሙንና የትምህርቱን ጊዜ ወደኋላ ተመልሶ ለመማረያ ወይም ለመዘጋጃ ለማግኘት ስለማይቻል ቍልቁትንትና ዘራት የወለደውን ፍዳ በትዕግሥት ከመቀበል በቀር ጸጸቱ ዋጋ አልነበረውም ። የበዛውም መንፈሳዊ ትምህርት ከመድቀቁ አላዳነም ።

ከዚህ ውጭ የአውሮፓ ሕዝብ ግን ከብሉይና ከሐዲስ ትምህርት አልፎ በዚህ ዘመን ለማስፋፋት የሚታገልበት የሕክምና ፣ የመሐንዲስነት የቤትና የመንገድ አሠራር የደንጊያ ቅርጽ የብረታ ብረት የባሩድ አሠራር ፈጽሞ ችላ ተብሎ የባለሥ ልጣኖቹ አሳብ በነዋሪው ዕውቀትና በመንፈሳዊው ትምህርት ብቻ እንደታሠረ ኖረ ።

አባቶቻችን ዕውቀትም ትጋትም የአካልና የመንፈስ ብርታትም እያላቸው ይኸን ጠቃሚ የሆነውን የዘመኑን ልዩ ልዩ ዕውቀት መማሩ አትቷቸው ሳይሆን አውቀው በንቀት የተዉት ይመስላል ። ምክንያቱም አብዛኛው ይህ ሁሉ እላይ ያመለከትነው ልዩ ልዩ የፍልስፍና የመሐንዲስነት የሕክምና ወይም የብረታብረት ሥራ የመነጨው ከተመረጠው ሕዝብ ከእሥራኤል ሳይሆን ከእሥራኤል ከማይወ ለዱ ከአሕዛብ ከፈረንጆች የተገኘ ነው ብለው ይሆናል ። በዚህም ላይ ጳውሎስ በመልእክቱ እኛካስተማርናችሁ ሌላ መልአክ እንኳ መጥቶ ቢያስተምራችሁ እን ዳትቀበሉ ብሎ ያወገዘውን ለዚህኛው ለሥጋዊው ትምህርት እንዲውል አድርገ ውት እንደሆነ አይታወቅም (1) ።

ደግሞ የዚህ የሥልጣኔ ባለቤቶች ፈረንጆቹ ግማሾቹ እንደ ፖርቱጋል እንደ ኤስፓኝ እንደ ፈረንሳዊ ያሉት ክርስቶስን ፪ ባሕርይ አለው የሚሉ ግማሾቹ እንደ እንግሊዞቹ እንደ ጀርመኖቹ ያሉት ማርያም አታማልድም የሚሉ ስለ እሱ እነር ሱም ዓርብ ሮብ አይጾሙም በኦሪት ሙሴ የከለከለውን የአሳማ ሥጋ ይበላሉ ሲባል ከነዚህ ጋር መቀራረቡ ከነዚህ መምህራን ትምህርት መቀበሉ ያቀፋቸዋል ። እነዚህን ከመሰሉ አረማውያን የሚገኘውን ትምህርት ከመቀበል አለመቀበሉን የሚመርጡ ይመስላል ።

ISIC

የሃይማኖቱንና የልማዱን ጉዳይ በትምህርት ከሚገኘው ጥቅም ጋር ለይቶ መረዳቱ ለዚያን ጊዜ አእምሮና አስተያየት ችግር ነው ።

እያደር የእስላሞቹ አደገኛነት እየከበደ ሲሄድ ወደፊት እንደምናነበው በግድ ከፖርቱጋሎቹ ግንኙነት እስኪመሠረት ድረስ የኛዎቹ ከፈረንጆቹ ሥልጣኔና ዕውቀት ለመራቅ እላይ ከጠቀስናቸው ምክንያቶች በተር በዚያን ዘመን አስተያ የት በቂ የሆነና የባሰ ብዙ ምክንያት አላቸው ። ቀድሞውኑ የክርስቶስን ባሕርይ ይከፍላሉ «ከፋልያን ክርስቶስ» ብለው ከሚጠሉዋቸው ሌላ ከፈረንጆቹ አዋቂዎ ችና ፈላስፎች ውስጥ ዴካርትስ የሚባል «ወደ እውነት ለመድረስ ከላይ በል ማድ የተቀበልነውን እውቀት አስወግደን በአዲስ መንፈስ መነሣት አለብን» ብሏል ። ስፒኖዛ የሚባለው «መላው ዓለም አምላክ ነው (Panthéisme) እንጂ ከዓለም የተለየ ለብቻው ተቀምጦ ዓለምን የፈጠረ ወይም የሚያስተዳድር አምላክ (Demiurge) የለም» እያለ ክህደት ያስተምራል ፤ ጋሊሊዮ ጋሊሌይ የሚባል «መሬት እንጂ ፀሐይ አትዞርም» ይላል የሚባለው ወሬ ከየመንገደኛው በተሰማ

(1) ገላትያ ምዕ. 1 ቍ. 7 - 9

ቊጥር ነገሩ እየሰቀጠጠ በቀድሞው ጥላቻ ላይ አዲስ ጥላቻ እንደሚጨምር ግልጽ ነው ።

ይኸም እንኳን በኢትዮጵያና በዚያው በአውሮፓም ቢሆን የኋላ የሕዝብና የሊቆች እንቅስቃሴ (Revolution) እያደር እስኪደመሰሰው ድረስ ይኸን የመሳሰለውን አሳብ አልፈው አልፈው ያፈለቁ ሰዎች በጳጳሳትና በነገሥታቱ ሥልጣን እየተያዙ ሲታሠሩም ሲገረፉም ኖረዋል ።

በቅርባችን ያሉት በዘርና በልማድ የሚቀርቡን ዓረቦችና ቱርኮች ዕውቀታቸው ከአውሮፖች ዝቅ ቢልም ለጊዜውና ላለንበት ደረጃ በቂ የሆነ ዕውቀት አላቸው ። የቀረው ቢቀር የባሩድ ሥራ ይችላሉ ። ነገር ግን እነርሱ ደግሞ ክርስቶስ አምላክ አይደለም አምላክም አይወለድም ስለሚሉ ግንኙነቱና ትምህርቱ ከፈረንጆቹ ጋር እንዳቃተ ከነዚህም ጋር ተማሪና አስተማሪ ሆኖ አብሮ ውሎ አድሮ በማኅበራዊ ኑሮ ተባብሮ ትምህርት የመቅሰሙ ነገር በቤተ ክህነቱም በቤተ መንግሥቱም ዘንድ አዳጋች ሆኖ ኖረ ። የፈረንጆቹን ሥልጣኔያቸውን ፤ ዕውቀታቸውን ሀብታቸውን ቢረዱትም «ምን ይደረግ ሀብት ጉትንት ዕውቀት ለአሕዛብ ተሰጠ ፤ ዘመን ያመጣው ነው ቿኛው ሺ የወለደው ነው» እያሉ የነዚያን ሥልጣኔ ከመናቅ በነርሱ አለመሰልጠን ከመጽናናት በቀር አዲስ የሥልጣኔ በር ሊከፍት የሚደፍር አልተገኘም ። ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ በኑሮ በልማድ የተሳሠረ በእምነት በአሳብ የተዋሐደ ስለሆነ ሁሉም የቆየውን ልማዳዊ ሥርዓት ላለማስደፈር ሲል የተያዘውን ነዋሪ ዕውቀት በቂ አድርጎ በመመልከት ለመከላከያ መድን ለሆነው ለብረታ ብረትና ለባሩድ ሥራ በጠቅላላው ለሥልጣኔ ፊቱን አዙሮ ዦርባውን በሰጠበት ዘመን ሳይታሰብ የግራኝ አህመድ ወረራ እንደ ጐርፍ ደርሶ ሁሉንም እንዳጥለቀለቀው ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

የጦሩ መከራ በየአለበት እያጥለቀለቀ ፋታ በነሣበት ሰዓት የተቀቡት ንጉሠ ነገሥት ታላላቆቹ ራሶችና ቢትወደዶች ፤ ዓቃቤ ሰዓቶችና ባሕር ነጋሾች የበዛውን ወግና ሥነ ሥርዓት ከብራቸውን ወደጐን ችላ ብለው ባጭር ታጥቀው ከባሕር ማዶ መምህራን እየቀጠሩ በጦር ትምህርት ጠንክረው አለመሠልጠናቸው የሰይፍ አመታት የጋሻ አመካከት በትጋት አለመማራቸው እንደሚቆጫቸው የታወቀ ነው ።

ይኸንን ሁሉ እናውቃለን ቢሉም ለመከላከያና ጠላትን ለማጥቂያ ደንበኛ መድን የሆነውን የዘመኑን የጦር መሣሪያ በባሩድ የሚተኰስ መድፍና ነፍጥ ሳያሰናዱ መቅረታቸው እንደሚጸጽታቸው እርግጥ ነው ። ዛሬ ግን ያለፈው የሰላሙንና የትምህርቱን ጊዜ ወደኋላ ተመልሶ ለመማሪያ ወይም ለመዘጋጃ ለማግኘት ስለማ ይቻል ዘንግተኞትና ነበሩት የወለደውን ፍዳ በተለማመት ከመቀበል በቀር ጸጸቱ ዋጋ አልነበረውም ። የበዛውም መንፈሳዊ ትምህርት ከውድቀቱ አላዳነም ።

## ምዕራፍ ፮

## የኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ደረጃና የሚገኝባቸው ምንጮች ።

የትምህርቱ ሁኔታና መጠን ባለፈው እንደተመለከትነው ሲሆን የሥነ ጽሑፉ ደረጃ ከዚያ ተለይቶ ለብቻው ተሻሽሎ ሊገኝ እንደማይችል የታወቀ ነው ። ስነ ጽሑፍ የሚወለደው ከትምህርት ነው ። ስለዚህ ትምህርቱን መንፈሳዊ ዝንባሌ ሲጫኑው የሥነ ጽሑፉ ምርትም ከመንፈሳዊነት ሊዘል አይችልም ።

በዚህ በ፲፭ኛውና በ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. በአውሮፓ ሳይቀር የፊውዳሊስም አስተዳደሩና የቤተ ክህነቱ ሥልጣን ተባብሮ እየከበደ ለሥልጣኔ እንቅፋት መሆኑ ባይካድም በዚሁ ጐን ቀድሞ የግሪክና የሮማ ሊቃውንት በእጅ ጽሑፍ እያዘጋጁ የተዉት ያስተዳደር ፣ የፍልስፍና ፣ የሲያንስ ፣ የሕክምና ፣ የቅርጽና የሥዕል ፣ የመሐንዲስነት ትምህርት በየቋንቋው እየተተረጐመ በማንተም እየተባዛ ዳግም ልደቱን (Renaissance) ሲያገኝ በኛ በኩል ደግሞ ከአክሱሞች ውድቀት ወዲህና በነዓምደ ጽዮን መንግሥት መካከል ባለው ጊዜ ዳግም ልደታቸውን ያገኙት በሥጋዊ ትምህርት ረገድ የክብረ ነገሥትና የታሪክ ነገሥት ጽሑፎች ናቸው ። በመንፈሳዊ ረገድ ከዚህ በፊት የጠቀስናቸው የሊቃውንቱ የነአፈወርቅ መጻሕፍት ሲሆኑ በዚሁ ጊዜ እንደ ተአምረ ማርያም እንደ ገድለ ጊዮርጊስ የመሳሰለው ከዓረብኛ ሲተረጐም ያገር ተ[illegible] የሆነው መነኩሴና ካህን ለጸድቃንና ለሰማዕታት በግዕዝ የሚደርሰው የግጥም ድርሰት ብዙ ነው ። ከነገሥታቱ ውስጥ ዘርዓ ያዕቆብ የመንፈሳዊ መጻሕፍት ደርሰዋል ። ዓፄ ናዖድ የማርያምን መልክና እንደዚሁም ስለማርያም የደረሱትን ቅኔ ስናነብ በጠቅላላው የሁሉም ዕውቀትና ዝንባሌ ለመንፈሳዊ ትምህርት መሆኑን እንገነዘባለን (፩) ።

በዚህ ምክንያት ብዙ የመንፈሳዊ መጻሕፍት በያይነቱ ሲኖረን ስለታሪክና ስለፍልስፍና ስለ አስተዳደር ስለኢኮኖሚ የተጻፈው በጥቂቱ ነው ። ጸሐፊዎቹ የቤተ ክህነት ዕውቀታቸውም መንፈሳዊ ከመሆን የተነሣ ለዚህኛው ጽሑፍ መጻ ከም እንደስንፍና ወይም ለከንቱ ነገር ጊዜን እንደማጥፋት ተቆጥሮ እንደሆነ አይታወቅም ። በቅድሚያ ፊልገው ካልተማሩትም ለመጻፍ ራሱ ችሎቱ አይገኝም ።

በዚህም ላይ በሠለጠኑት አገሮች ደረጃ የእጅ ጥበብ አዋቂ ፣ የሕንፃ መሐንዲስ እንደሌለ ሁሉ የነገሥታቱንና የታላላቅ ሰዎቻችንን መልክ በደንገያ ላይ የሚሊዎች ሙያችውና ርቀታቸው እንደነርሱ ባይሆንም ከነርሱ ያነሱ ስለአልነበሩ መሆኑን ዛሬ እናውቅም ። በአጻጻፍ ረገድ የግል የሕይወት ታሪክን መጻፍ የመልክ ምን መሳይ ንና የአቋቋምን ሁኔታ በዝርዝር በጽሑፍ ቀርጾ ማስፈሩም ያን ጊዜ ስለአልተለ

(፩) የኢ.ት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. ፰ ገጽ 291 - 303

መደ ዘርዓ ያዕቆብ ቀይ ይሁኑ ጠይም ወፍራም ይሁኑ ቀጭን ረዥም ወይም አጭር መሆናቸውን ለይተን አናውቅም ።

ነገር ግን ይኸን የመሳሰለው በአውሮፓ የሕይወት ታሪክ ላይ የምናውቀው የሥልጣኔ መልክ እንደዚሁም በኛው ዘንድ በአክሱም ዘመን የታየው ሥልጣኔ ይጉደል እንጂ ከአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ዠምሮ እስከ ግራኝ አህመድ እነሣሥ ድረስ በዚያው በመጠኑ የሥነ ጽሑፍ እርምጃ ባዲስ ኃይል እንደገና ተቀ ስቅሶ መታየቱ ግልጽ ነው ።

ባገሪቱ በዚህ ዘመን የተደረሱትንም የተተረጐሙትንም መጻሕፍት ስንመለ ከታቸው ከሥጋዊው መንፈሳዊው እንደሚበረክት ሁሉ ከሊቃውንቱም ውስጥ የላቲንና የግሪክ ቋንቋ (ጽርእ ሮማይስጥ) ከሚያውቀው ዓረብኛ የሚያውቀው በር ክቶ ይታያል ።

የዚህ ምክንያት ግልጽ ነው ። ኢትዮጵያ ክርስትና ከተቀበለችበት ጊዜ ወዲህ ሃይማኖትን የሃይማኖት አባቶችን የተቀበለችበት ዓይነተኛው መደብ የማርቆስ ወንበር ያለበት የእስክንድርያ ከተማ ነው ። በዚህ ከተማ ከጥንት ከእስክንድር ወረራ ዠምሮ የግሪክ ቋንቋና ሥልጣኔ ቢበረክትም በመጨረሻ ግን ከዓረብ ወረራ ወዲህ የአገሩ ቋንቋና ሥልጣኔ ዓረብኛ ስለሆነ በመንበረ ማርቆስ የሚቀመጡት የፓትሪያርኩና ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩት የግብጻውያን ጳጳሳት ቋንቋቸው ዓረብኛ ነው ።

ISIC

በዚህ ምክንያት በጽርዕ ወይም በሮማይስጥ አለዚያም በዕብራይስጥ የተጻፈ የክርስትና መጻሕፍት የጻድቃንና የሰማዕታት ገድልና ድርሳን በግብፅ አገር ወደ ዓረብኛ በብዛት ሲተረጐም ከዚያ ላይ ደግሞ የኛዎቹ ሊቃውንት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ እየተረጐሙ ያስፋፉታል ።

በዚህ ምክንያት ክብረ ነገሥት ፤ ዜና እስክንድር ፤ ተአምረ ማርያም ፤ ገድለ ፋሲለደስ ፤ ገድለ ዮስጦስ ፤ ገድለ ቴዎድሮስ ፤ ገድለ ፊቅጦር ፤ ገድለ ገላውዴዎስ እነዚህን የመሳሰሉት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ተተረጐሙ ። በዚሁ ጐን ደግሞ ላገር ተወላጆቹ ጻድቃን ለነአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ፤ ለነአቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤ ለነአቡነ ፊልጶስ ፤ ለነአባ ሳሙኤል በቀጥታ ያገር ተወላጁ ካህን በግዕዝ የሚታመንም የማ ይታመንም ታሪክ እየጨመረ ገድል ይደርሱላቸዋል ።

በዚህ ዘመን በተለይ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኙት የቤተ ክህነትና የቤተ መንግ ሥት ባለሥልጣኖች ፤ ዓቃቤ ሰዓቱ ፤ ንቡረ ዕዱ ፤ ቄስ ዓፄው ፤ ጸሐፌ ትእዛዙ ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ጋር ከሥጋዊው ሥራ ይልቅ አሳባቸውን የሚይዘው የመንፈሳዊው ነገር ከመሆኑ የተነሣ በየዘመኑ ከሥጋዊው ይልቅ የመንፈሳዊው የድርሰት ምርት በጣም በርክቶ ይገኛል ። ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ወዲህ በተለይ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፈ ሚላድ ፤ መጽሐፈ ሥላሴ ፤ መጽሐፈ ባሕርይ ፤ መጽሐፈ ብርሃን የሚባሉትንና ሌሎችንም እየደረሱ ሲያስፋፉ በየመጻሕፍቶቻቸው የሚገል ጹት ስለቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ፤ ስለበዓላት አከባበር ስለጌታ ልደት ስለሥላሴ አንድ ነትና ሦስትነት ስለማርያም ክብር ሲሆን በዚሁ አንፃር የጌታን ልደት የሚክዱትን

አይሁዶች ከክርስትና ሃይማኖት እየራቁ ይስኩ ፡ ጉዳሌ ፡ ዲና ፡ ማካውዜ ፡ ታውፍንት በሚባሉ ጣዖታትና ዛሮች የሚያመልኩትን ኢትዮጵያውያን ያወግዛሉ (1) ።

ከበረከተው ገድልና ድርሳን መካከል ሥጋዊ ወይም ታሪክ ነክ ሆኖ ለዛሬ ዘመን ያረቅ ታሪክ የሚያገለግለው ፡ ፩ኛው ከዚህ በፊት የጠቀስነው ክብረ ነገሥት የተባለው ነው ። በመጽሐፉ ላይ ጽሑፉ ከእስክንድርያ ከግርቆስ ወንበር ባዔ ላሊበላ ዘመን ወደኢትዮጵያ መጥቶ ሳለ በዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በእንደርታው ሹም አሳሳቢነት የአክሱሙ ንቡረ ዕድ ይስሐቅ ከጓደኞቹ ሊቃውንት ከነይምርሐነ አብ ጋር ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ እንደተረጐመው ይገልጻል ። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የንግሥተ ሳባ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ ከሰሎሞን ምኒልክን መጽነሷ ፡ ወደገሯ ተመልሳ መውለዷ ፡ ምኒልክ ካደገ በኋላ አባቱን ሰሎሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ ፡ ከዚያ ሲመለስ ጽላተ ሙሴን በካህናቱ በነሳዶቅ አማካይነት አስወስዶ ወደ አገሩ ገብቶ የመገመሪያው የኢትዮጵያ ሰሎሞናዊ ንጉሥ ሆኖ መንግሡን ይተርካል ።

ቀጥለው የሚገኙት የታሪክ መጻሕፍት ዓፄ ዓምደ ጽዮን በሰበርዲን መሪነት ተባብረው የመጡትን የአዳል ባላባቶች ተዋግቶ ያሸነፈበት የጦርነት ታሪክ ከዚያ የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብና የዓፄ በእደ ማርያም ረዘም ያለው የዓፄ እስክንድርና የዓፄ ናዖድ አጫጭሩ ዜና መዋዕል ይገኛሉ ። እንደዚሁም በትንሹ ለዓምደ ጽዮን ለይስሐቅ ፤ ለዘርዓ ያዕቆብ በዘ[illegible]ማርኛና ግዕዝ በተደባለቀበት ቋንቋ የተደረሱ ግጥሞች አሉ (2) ።

ይኸም ሁሉ ሆኖ የሥጋዊና የመንፈሳዊው መጽሐፍ ድርሰቱም ትርጉሙም ተጨምሮ ተደምሮ ቢመዛዘን የሥጋዊው ከመንፈሳዊው ከመቶ አምስት (5%) የሚበልጥ አይመስለኝም ። ሥጋዊውንም መንፈሳዊውንም መጻሕፍት የኢትዮጵያ ሊቃውንት አሜን ብለው አምነው በደስታ የሚቀበሉት ራሳቸውም ተምረው ለወገናቸው የሚያስተምሩት መጽሐፉም ትምህርቱም ጌታ ከተወለደበት ከሞተበትና ከተቀበረበት ሐዋርያት ካስተማሩበት ከኢየሩሳሌም ወይም የተዋሕዶ ሃይማኖት ከመነጨበት ከእስክንድርያ ከዚያ ደግሞ ሲበዛ የቆስጠንጢኖስና የእናቱ የቅድስት እሌኒ ከተማ ከሆነው ከቍስጥንጥንያ ወይም የሰማዕታት የነገላውዴዎስ አገር ከሆነው ከአንጾኪያ የፈለቀ ሲሆን ነው ።

ከነዚህ አገሮች የመጣው መጽሐፍ ደራሲው የክርስቶስን ባሕርይ የማይከፍል ተዋሕዶ መሆኑ ሲታወቅ ክርስቶስ አምላክ አይደለም በሚሉ በአርዮሳዊነት ወይም በንስጥሮሳዊነት የማይጠረጠር መሆኑ ሲታወቅ አሜን ብለው ይቀበሉታል

ነገር ግን በዚህ በ፲፭ - ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. እላይ ስማቸው ከተጠሩት የክርስትና መደብ ከሆኑት ከተሞች ይልቅ ሥጋዊ ትምህርትና ዕውቀት የገነኑባቸው ልዩ ልዩ ትምህርት የሚገበዩባቸው ከተሞች ሮማ ፡ ሊስቦን ፡ ፓሪስ ፡ ለንደን ፡ በር

(1) የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. ፴

(2) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. ፲ - ፲፭ ምዕ. ፴ - ፴፯

ሊን ናቸው ። ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ከነዚህ አገሮች ጋር ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ የክርስቶስ ባሕርይ የኛዎቹ አንድ ነው እነዚያ ሁለት ነው በመባባል በጠብ መለያየት ከሆነ ወዲህ ከነዚህ በኩል ለሚገኘው ለማናቸውም ጥሩ ጥሩ የቴክኒክና የአስተዳደር ትምህርትና ዕውቀት ዋጋ ሰጥቶ ለመቀበል የሚደፍር የለም ።

ኢትዮጵያ የምታምናቸውና የምታፈቅራቸው አገሮች የሃይማኖት አባትና መንፈሳዊም ሥጋዊም ትምህርት የምታገኝባቸው ከተሞች እስክንድርያ ፣ ኢየሩሳሌም ፡ አንጾኪያ ፡ ቍስጥንጥንያ መዠመሪያ በዓረብ ቀጥሎም በቱርክ ሡልጣኖች ውስጥ ቢደመሰሱም ሃይማኖትን የተንተራሰውን መሠረታዊ አሳቧን ለውጣ የምዕራባውያንን ሥልጣኔና ትምህርት ለመቀበል አሳቧን አልለወጠችም ።


በዚህ ምክንያት በምዕራብ በኩል ምንም ዓይነት እንደ ሻርለማኝ ያለ ወይም እንደ ሻርል ፭ኛ ያለ ንጉሠ ነገሥት ቢነሣ በኢትዮጵያ የቆስጠንጢኖስን ወይም የዳግማዊ ቴዎዶስዮስን ራቅም ብሎ የዳዊትንና የሰሎሞንን ያህል ታውቀው አይከበሩም ። ምንም ዓይነት አዋቂና ፈላስፋ ከነዚህ ወገን ስሙ ቢነሣ ካቶሊክ ነው ከተባለ በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ በኩል ከመናቅና ከመወገዝ አያልፍም ።

ነገር ግን ይህ የቤተ መንግሥቱም የቤተ ክህነቱም መሪዎች መሠረታዊ ስሜትና እምነት ሆኖ ከይኩኖ አምላክ ዠምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ድረስ ከዘለቀ በኋላ በየጊዜው እየሸፈቱና እየተዋጉ የሚያስቸግሩት የወላስማ ባላባቶችና አዳሎች ብዙ ርዳታ በየጊዜው ከዓረብ ከግብፅ ማግኘታቸውና ማስጋታቸው እያደር ሲታወቅ በግድ ይኸንን ሃይማኖታዊ የጠብ ስሜት አቀዝቅዞ ከፖርቱጋል ጋር ግንኙነት ሲደረግ ወደፊት እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፯
## የዘመኑ ጸሐፊና የቀለም ሰው

በኢትዮጵያ በዚህ ባለንበት ዘመን እንደምንረዳው ሁሉ በዚያ የፈረንጅ ዕውቀትና ትምህርት በማይፈለግበት በሩቁ ዘመን ያሉት የቤተ ክህነት ሊቃውንት ብዙ ናቸው ። በቤተ ክህነት አገልግሎት ብቻ የተጠመዱትን መነኮሳቱን ቀሳውስቱን ፣ ደባትሩን ፣ ዲያቆናቱን ወደጐን ትተን የታሪክን መጽሐፍ የሚከታተሉ የቤተ መንግሥት ወግና ሥርዓት የሚያውቁ በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ሞልተዋል ። እነርሱም የዘመኑ የቀለም ሰዎች የሚባሉት ናቸው ። ነገር ግን የቀለም ሰው ወይም ሊቅ የተባለው ሁሉ ጸሐፊ ሊሆን አይችልም ።

የዘመኑ ትምህርት ንባብና ቅኔ ዜማና መጻሕፍት ከአንደበት ወደ አንደበት እየተላለፈ በቃል እየተደመጠ የሚማሩት ነው እንጂ እንደዛሬው ዘመን አውሮፓዊ ትምህርት ከወንበር ላይ ተቀምጦ ጠረጴዛ ተደግፎ በእጁ ብረት ብርዕ ጨብጦ ከመምህሩ የሚሰማውን እንዳይጠፋው በማስታወሻ በደብተር ላይ እየጻፈ የሚማር የለም ። ስለዚህ ብዙ የመጻሕፍት ሊቃውንት በብሉይና በሐዲስ በቅኔና በዜማ ትም



ምንት፡ይዜህር፡ኃያል፡በእከዩ።
ወይዔምፅ፡ኵሎ፡አሚረ።
ኃጢአተ፡ሐለየ፡ልብከ።
ከመ፡መላጼ፡በሊሕ፡ገበርከ፡ሕብለ።
አፍቀርከ፡እኪተ፡እምሠናይት።
ወትዔምፅ፡እምትንብብ፡ጽድቀ።
ወአፍቀርከ፡ኵሎ፡ነገረ፡ወልሳነ፡መስሐተ።
በእንተዝ፡ይነሥተከ፡እግዚአብሔር፡ለዝሉፉ።
ወይመልኀከ፡ወያፈልሰከ፡እምቤትከ።
ወሥርወከኒ፡እምድረ፡ሕያዋን።
ይርአዩ፡ጻድቃን፡ወይፍርሁ።
ወይሥሐቁ፡ላዕሌሁ፡ወይበሉ።
ነዋ፡ብእሲ፡ዘኢረሰዮ፡ለእግዚአብሔር፡ረዳኢሁ።
ወተአመነ፡በብዝኀ፡ብዕሉ።
ወተኀየለ፡በከንቱ።
አንሰ፡ከመ፡ዕፀ፡ዘይት፡ሠመር፡ውስተ፡ቤተ፡እግዚ
ወተወከልኩ፡በምሕረቱ፡ለእግዚአብሔር።
ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም።
እገኒ፡ለከ፡ለዓለም፡እስመ፡ገበርከ፡ሊተ።

ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበረው የብርዕ አጣጣል የሐረግና የሥዕል ዓይነት ። ከዳዊት መዝሙር አንዱ ክፍል ።

ሀርታቸው የተደነቁት ከመካከላቸው በደንብ ማንበብ ማስነበብ ሲችሉ ስማቸውን መጻፍ የሚያዳግታቸው እንደነበሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ተመልክተናል ። ፊደል ማን በብ መጻፍን አያስችልም ፤ መጻፍም የአጻጻፍን ዘዴ በራሱ አይሰጥም ። ሦስቱንም ለየብቻ ይማሩ ዘንድ አስፈላጊ ነው ።

ስለዚህ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከጸሐፌ ትእዛዙ በታች ሥራቸው ጸሐፊነት የሆነ በኋለኛው ዘመን ቁም ጸሐፊ እንደሚባሉት ያሉ ከመንግሥት ቀለብ እየተሰ ጣቸው የሚጽፉ አሉ ። ጸሐፌ ትእዛዙ አብዛኛው ጊዜ የንጉሡን ዜና መዋዕል ማዘጋ ጀት የራሱ ተግባር ስለሆነ እስከ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ድረስ የሚገኘው የነገ ሥታት ዜና መዋዕል አብዛኛው በየጸሐፍተ ትእዛዛቸው የተዘጋጀ ነው ።

ሆኖም በጠቅላላው ጸሐፌ ትእዛዙ ከነጭፍሮቹ ለዚህ ለጽሕፈት ተግባሩ ሆኖ የተመደበ ነው ለማለት ነው እንጂ ከርሱ ውጭ ሌሎቹ አይጽፉም ለማለት አይደለም ።

እንደ እጨጌ ዕንባቆም ፤ እንደ ንቡረ እድ ይስሐቅ ያሉት ከዓረብኛ ቋንቋ ከመተርጐም ጋር ራሳቸው መንፈሳዊ መጽሐፍ እየጻፉ የሚደርሱ የብዕራቸው አጣጣል ያማረ ሞልተዋል ። በነርሱ እጅ በየዘመኑ የተደረሰው ወይም ከነባሩ መጻ ሕፍት እየተገለበጡ የተጻፉት መጻሕፍት በአውሮፓ በታላላቁ መጻሕፍት ቤት የተቀመጡት ፤ በሐረግና በድጕስ ያማረው በቀይና በጥቁር ቀለም እየተሸበረቀ የተ ጻፈው ሁልጊዜ የተመልካችን ዓይን እንዳስደሰተ ነው ።

ISIC

ኮንቲ ሮሲኒ ሰብስበው ባሳተሙት የገበዘ አክሱም መጽሐፍ ላይ የብዙ ዓቃቤ ሰዓት ፤ የንቡረ እድ ፤ የቄስ ዓፄ ፤ የጽራግ ማሰሬ ፤ የቀኝ ጌታ ፤ የግራ ጌታ ፤ የሊቀ መጣኔ ስም ተጠቅሷል ። እነዚህም ሲበዛም ሲያንስም የቀለም ሰዎችና ሊቃውንት ናቸው ። በዚህ ስም ሳይጠሩ ቢትወደድ ፤ ራስ ሕዱግ ፤ ራስ ፤ ጸሕፈ ላም ፤ አቃጽን ከሚባሉትም ውስጥ የተማሩ እንደሚገኙባቸው ባለፈው አመልክተናል ።

በዚሁ መጽሐፍ በተለይ በገጽ ፳፰ በዓለ መጽሐፍ ሃኖ ፤ በገጽ ፳፱ በዓለ መጽ ሐፍ ጊዮርጊስ ፤ በገጽ ፴፪ በዓለ መጽሐፍ ዮሐንስ ፤ በገጽ ፴፫ በዓለ መጽሐፍ ያዕ ቆብ ፤ በገጽ ፴፭ በዓለ መጽሐፍ ሃይዞ ፤ በገጽ ፴፯ በዓለ መጽሐፍ ጴዋ ፤ በገጽ ፴፰ ጸሐፊ ዘርዓ ማርያም ይላቸዋል (1) ።

በዓለ መጽሐፍ ሲል የመጽሐፍ ጌታ ባለቤት ማለቱ ነው ። እርሱም ደራሲም ተርጓሚም አስተማሪም ሆኖ ስለ መጽሐፍ ጉዳይ ተጠያቂነቱንና የቀለም ሰውነ ቱን የሚያሳይ ነው ። በዓፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ላይ አባ ተክለ ማርያም የሚባ ሉትን መምህረ ነገረ ነገሥት ይላቸዋል ። የቤተ መንግሥት ወግና ሥነ ሥርዓት የሚያውቁ ማለቱ ነው (2) ።

እንግዲህ ለዛሬ ታሪክ አሰባሰብ የሚረዳውን ታሪከ ነገሥትና ዜና መዋዕል የሚባለውን አልፎ አልፎ ታሪክ ጠቀስ የሆነውን የሰማዕታትና የጻድቃን ገድልና ድርሳን እየጻፉ ወደ ጊዜያችን ያደረሱ እነዚህ ናቸው ።

(1) Documenta ad illustrandam Historiam-I Liber Axumae ተመልከት ።

(2) Chronique de Gelawdeos-W. El CONZELMAN ገጽ 106

እነዚሁ ጸሐፊዎች እንደ አትማቸው አብስለው የተማሩት ባለፈው ምዕራፍ የጠቀስነውን ብሉይና ሐዲስን ከዚያም የሊቃውንትን መጽሐፍ ስለሆነ በአጻጻፋቸው እንደምስክር እየጠቀሱ ለጽሑፋቸው ማስረጃና መደገፊያ የሚያደርጉት የሙሴን ፤ የዳዊትን ፤ የሰሎሞንን ድርሰት በሐዲስ ወንጌልን ፤ የጳውሎስን መልእክት ወይም ቄርሎስን ፤ አፈወርቅን ነው ። በነርሱ ጽሑፍ ውስጥ እንሖሜር ፤ እንአሪስቶትል ፤ እንቪርጅል ሥፍራ የላቸውም ። የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን የነጎርጎርዮስ ፤ የነቶማስ ዳኪን ጽሑፍ ተፈላጊ አይደለም ። እነዚያን አሕዛብ እነዚህን የክርስቶስን ባሕርይ የከፈሉ በሚለው የጥላቻና የንቀት ስሜት ራሱ ትምህርታቸው አብሮ ስለተጠላ አይታወቅም ።

ስለዚህ በዚህ ዘመን ያሉት የቀለም ሰዎቻችን ከሥር ከመሠረት ዝምር የትምህርታቸው መሠረት ብሉይና ሐዲስ ወይም የነዚሁ ዘርፍ የሆኑ መጻሕፍት ከመሆን የተነሣ የጽሕፈታቸውም መሠረት ይኸንኑ ዓላማ ሳይለቅ እስከ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ደረሰ ። እኚህን ሰው መጥቀሳችን የቀድሞዎችን ጸሐፍተ ትእዛዛት መልክ እንዳለ ይዘው ባጻጻፋቸውም እነዚያን የቀድሞዎቹን ጸሐፌ ትእዛዞች የሚያሳዩ የፈረንጅ ዕውቀትና ትምህርት ያልተበረዘባቸው ንጹሕ የመጨረሻ ጸሐፌ ትእዛዝ ስለሆኑ ነው ። በርሳቸው አጻጻፍ ውስጥ የቀድሞዎቹን ጸሐፍተ ትእዛዞች የአጻጻፋቸውን ሥዕል እንመለከታለን ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንደ ቀድሞዎቹ ጸሐፍተ ትእዛዝ ባንድ ወገን የራጉኤል አለቃ በኋላ ደግሞ ንቡረ እድ ሆነው የቤተ ክህነትን ሥልጣን ሲይዙ በዚያው ጐን የዳግማዊ ምኒልክ ጸሐፌ ትእዛዝ ሆነው የመንግሥት ባለሥልጣን ናቸው ። በዚሁ በጸሐፌ ትእዛዝነት ተግባራቸው ምክንያት ለዛሬ ዘመን የዳግማዊ ምኒልክ ታሪክ መሠረት የሆነውን ዜና መዋዕል አዘጋጅተዋል ።

ISIC

የቃል አስካካቸው የመጻሕፍት አወራረሳቸው መንገዱና ስልቱ ከነዚያው ከቀድሞ ጸሐፊዎች በትክክል ሲያያዝ የመጣ ነው ። ትንሽም ቢለያይ የእርሳቸው የቀለም ወዝ በመስጠትና በመዘርዘር የነዚያ በማሳጠር የርሳቸው አግርኛ ሲሆን የነዚያ በግዕዝ መሆኑ ነው ።

በዚሁ በዳግማዊ ምኒልክ የታሪክ መጽሐፋቸው በምዕራፍ ፳፫ የዓድዋን ጦርነት በተረኩበት ላይ «ኢጣሊያኖች አጥብቀ ሽሽት ጸናባቸው» ካሉ በኋላ ለዚህ እንደምስክር አድርገው ያቀረቡት «በዚያ ከፉ ወንጀልን የሚሠሩ ይወድቃሉ መሸሽ እንጂ መቆምም አይችሉም» የሚለውን የዳዊት መዝሙር ነው (1) ። ንጉሠ ነገሥቱ ሐረርጌ ዘምተው አሚር አብዱላሂ በሰላም እንዲገባ ተጠይቆ እምቢ ያለውን ያነጣጠሩት «ወአግዘፈ ልበ ለፈርዖን» ከሚለው ከኦሪት ጋር ነው (2) ።

ስለዚህ ከይኵኖ አምላክ ዝምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መገመሪያ ድረስ አንዱ በማርዘም ሌላው በማሳጠር አንዱ የንግግር ወዝ በመስ

(1) «ሕየ ይወድቁ ገብርተ ዓመጻ ይሰደዱ ወኢይክሉ ቀዊመ» የዳዊት መዝሙር 36 ቍ. 13 ።
(2) ኦሪት ዘፀዓት ምዕ. 9 ቍ. 12 ። ታሪክ ዘመን ዘዳግ. ምኒልክ ምዕ. 36 ገጽ 140 ።

ጠት ሌላው በደረቁ በመጻፍ ይለያያሉ እንጂ የሁሉም የአጻጻፍ አስተያየትና አስተሳሰብ ወደ መንፈሳዊ ያዘነበለ ሆኖ ሁሉም ከብሉይና ከሐዲስ ታሪክና አነጋገር ጋር የተዛመደና የተመሳሰለ ነው ።

የውጭን አገር አጻጻፍ ካለማወቅ የተነሣ የግሪኮችና የሮማውያኖቹ የቅርቦቹ የአውሮፓና የዓረቦቹ ጸሐፊዎች የአጻጻፋቸው ስልት የቃል አደራደራቸው ደንቡና ሥርዓቱ ከየመጽሐፉ ተተርጉሞ በትምህርት መልክ ስለአልተወሰደ ከመንፈሳዊው ጽሑፍ ውጭ የሥጋዊና የታሪክ ነክ የሆነው አጻጻፍ ሁሉ ከማጠሩ በላይ ዝቅተኛ ደረጃን የያዘ ነው ።

በየጽሑፉ ላይ ደራሲው ትክክለኛ ስሙን ዓመተ ምሕረቱንና ቀኑን መፃፉ መር ስለሚያቅተው በሚገኙት የታሪክ ጽሑፎች ሁሉ በተለይ እስከ ዓፄ ሠርፀ ድንግል ያሉት ያብዛኞቹ የደራሲያቸው ስም የማይታወቅ የተደረሱበትም ዘመንና ቀን ስለአልተጻፈ ሁልጊዜ እንዳጠራጠረ ነው ።

ወደፊት ከምዕራፉ ላይ ስንደርስ በትክክል እንደምንረዳው ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤልም ለልጁ ለዮሐንስም ደብዳቤ ለመጻፍ ባሰቡበት ሰዓት ከዚህ በፊት ለፈረንጆች ነገሥታት መጻፍና ያጻጻፉ ዓይነት ስለአልተለመደ ስለአድራሻውና ስለአርእስቱ በደብዳቢው ውስጥ ስለሚጨመረው አነጋገር ተቸግረው ስለነበረ ራሱ መላክተኛ ሆኖ የመጣው እንግዳው አልቫሬጽና በኢትዮጵያ ብዙ ዘመን የኖረው ኮቪልሐአ ከዓቃቤ ሰዓቱ ጋር ተጨምረው ደብዳቤው በማኅበር መጻፉን ከደብዳቢው ውስጥ ለጥቅስ የሚገባውን እየመረመሩ የሚያቀርቡ ሌሎች ሊቃውንት ተሰብስበው እንደነበረና አንዱን ደብዳቢ ለመጻፍም ብዙ ቀን እንደፈጀ አልቫሬጽ ወዳገሩ ሲመለስ ባዘጋጀው መጽሐፉ ላይ ያወሳል (1) ።

እንደዛሬ ያን ጊዜ በጸሐፊነት ለመሠልጠን ከሠለጠኑ አገሮች ጽሑፍና ጸሐፊዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ ያስፈልጋል ። የራስንና የነዚያን እያስተያዩ በሁለቱ አጻጻፍና አቀራረብ መካከል ያለውን ልዩነትና የራስን ጉድለት አውቆ በነዚያ እየተመሩ የራስን አባባልና የአጻጻፍ ዘይቤ ሳይለቁ መማር ይቻላል ።

ይኸን ለማድረግ ደግሞ ለትምህርቱም ለአጻጻፉም ዋጋ መስጠትንና ነፃነትንም ያስፈልጋል ። ነገር ግን የዚያን ዘመን ጸሐፊ ከነበረው የአጻጻፍ መሥመር እንዳይወጣ ችሎቱም ነፃነቱም በቆየ የእምነትና የልማድ ሰንሰለት የተያዘ መሆኑ አይጠረጠርም ። ገድልና ድርሳን ለመጻፍ መልካ መልክ ለጸድቃንና ለሰማዕታት ቢደርስ ማናቸውንም መንፈሳዊ መጽሐፍ ቢተረጉም አይከለከልም ፤ እንዲያውም ሊመሰገንበት ይችላል ።

ነገር ግን ከዚህ ውጭ ታሪክ ነክ የሆነውን ንጉሡ በፈቃዱና በትእዛዙ ቀለብና ሹመት እየሰጠ የራሱና ያባቶቹ ክብርና ሥልጣን በማይነካበት መንገድ በመንፈሳዊው ጽሑፍ ተንተርሶ ካላስጻፈው በቀር አንድ ሰው በግሉ ተነሥቶ በፈቀደውና በመሰለው አስተያየትና አነጋገር ያገሪቱንና የነገሥታቱን ሐቀኛ ታሪክ ለመጻፍ

(1) Verdadeira informacao das Terras.. ...... F. Alvarez ምዕ. 106 ተመልከት

ችሎታም ነፃነትም የለውም ።

ነገሥታቱም ከገራቸው ያልወጡ የውጭውን አገር የሥነ ጽሑፍ እርምጃ ያልተ
ገነዘቡ በአስተዳደር ይሁን በጦር ድርጅት በአለባበስ ይሁን በሥነ ሥርዓት በንግድ
ይሁን በገንዘብ ቁጠባ አመራር ያገራቸውንና የውጭውን አገር እመዛዝነው ያለ
ውን የጉድለት ልዩነት ተገንዝበው ለማሟላት የማይመኙ በመሆናቸው የራሳቸው
ንም ሆነ ያባቶቻቸውን ዜና መዋዕል ያጻፉት ባጠረ ያጻጻፍ ፆረጃ ወይም በከንቱ
ቃለ አጋኖ የበረከተበት ሆኖ ሐቀኛው የጽሑፍ አቀራረብ ወይም ለዛሬ ዘመን አስ
ፈላጊ የሆነው የንጉሡ የልጅነትና የወጣትነት የሕይወት ታሪኩ የመልኩ ቅርጽ ፣
የቁመቱ ልክ ወደ ጐን ቀርቶ ይገኛል ። የራሷ ያገራቱም ጠቅላላ ታሪክ የሚባለው
የነገሥታቱ ታሪክ ብቻ ሆነ ።

በዚህ ምክንያት ከዓፄ ሠርፀ ድንግል በፊት የነበረው ታሪክና ጦርነት
ነክ የሆነው ሁሉ የጽሑፍ አዘመራሩ ምርት የሚፈለገውን ያህል ለዛሬ አንባቢና
ጸሐፊ ለማጥገብ አይችልም ። የነዓምደ ጽዮን የነዘርዓ ያዕቆብ ፣ የነበእደ ማርያም ፣
የነናዖድ የዘመን መንግሥታቸው ታሪክ ተጽፎ በሚገኘው ዜና መዋዕላቸው ምክን
ያት በትንሹ ሲታወቅ በነርሱ መካከል ያሉት የነሠይፈ አርዕድ ፣ የነዳዊት ፣ የነይ
ስሐቅ ብዙ ላገር የሠሩት ሥራ እንዳለ ሲታወቅ እንደዚሁ ተዘሎ ቀርቷል ። ወይፈ
ትም ከዚህ ቦታ ይገኛል ተብሎ ተሰፋ የሚጣልበት የታሪክ ምንጭ የሚገኝ አይመ
ስለኝም ። በዚያን ጊዜ ያልተጻፈ ከሆነ ታሪክ እንደ ቅኔ ከአእምሮ ሊፈልቅ አይች
ልምና እንደዚሁ መቅረቱ አሳዛኝ ነው ።

እላይ እንዳመለከትሁት ተጽፎላቸው የሚገኘውም የጸሐፊው ስም ስለአልተ
ጠቀሰ ዓመተ ምሕረቱም ስለአልተመለከተ በድካም ያዘጋጀው ጸሐፊ ስሙ እንደተ
ቀበረ ቀርቷል ። የጽሑፉን ዘመን ብዙ ሊቆች የፊደሉን አጣጣል በማመዛዘን ብቻ
የተቀራረበ ዘመን መድበውለት ይገኛል ።

ለጻፉት የታሪክ መጽሐፍ ምንም ዓመተ ምሕረት መጻፍ የማይወዱ ሲኖሩ
አንዳንዶቹ ደግሞ ምናልባት ዓረብኛና ዕብራይስጥ የማያውቁ ወይም ወደ ግብፅና
ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ዕውቀት ቀስመው የተመለሱ ይሁን ባይታወቅም የጻፉበ
ትን ጊዜ ለማረጋገጥ ሲሉ ላንዱ ጉዳይ ዘመን በዘመን ላይ በመደራረብ ዓለም በተፈ
ጠረ በዚህን ያህል (1) ክርስቶስ ሥጋ በለበሰ በዚህን ያህል (2) ሰማዕታት በአለቁ
በዚህን ያህል (3) እያሉ ከአስፈላጊው በላይ ዘመን ያራርበው ያቀርባሉ ። ግማሾ
ንጉሡ ከነገሠበት ዓመትና ከወሩ ጋር አነጣጥሮ ያመጣቀል ።

ለምሳሌ ከሁሉ ጸሐፊ በተሻለ መልኩ ያዓፄ ገላውዴዎስን ዜና መዋዕል የጻፈው
ስሙን የማናውቀው ጸሐፊ እዓፄ ገላውዴዎስ የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን

(1) ዓመተ ዓለም በ5500 ዓመት መሠረት
(2) ዓመተ ሥጋዌ ይኸውም ዓመተ ምሕረት ማለት ነው ።
(3) ዓመተ ሰማዕታት የሚባለው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ክርስቲያኖች በክርስቶስ እምነት ምክን
ያት እየተሳቀዩ ከሞቱበት ዠምሮ

አሠርተው ሲጨርሱ ለሊቀ ሠራዊት አፈወ ድንግል ዕልቅናውን የሰጡበትን ጊዜ ለመግለጽ እንደዚህ ይላል ።

ሀ በሳብእ ወርኀ እምሃሌ ሉያ (1)

ለ/ በ፸፻፵ወ፬ እምዓመተ ዓለም (7044) (2)

ሐ/ በ፲፭፻፵ወ፬ እምትሥጉተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ (3)

መ/ በ፲፪፻ወ፷፰ ዓመተ ሰማዕታት (4)

ሠ/ በ፱፻ወ፷፩ ዓመተ ተንባላት (5)

ይኸው ጸሐፊ አፄ ገላውዴዎስ ከኑር ጋር ተዋግተው የሞቱበትን ደግሞ ሲያወሳ በሌላ ሥፍራ የኑርን እንሣሥ የሰሙበትን ጊዜ እመ ፸፻፵ወ፱ ዓመተ ዓለም ወእመ ፲ወ፱ ዓመተ መንግሥቱ ይልና ተዋግተው የሞቱበትን እመ፳ወ፯ ለመጋቢት ሳብእ ወርኀ እም አውራኂነ ወሳልስ ወርኀ እም አውራኃ ሥርዓቶሙ ለሮም እያለ አበጥሮ ይጽፈዋል ። የሞቱበት ወር ፳፯ መጋቢት በኢትዮጵያ አቈጣጠር ከመስከረም ዠምሮ ሲቆጠር ሰባተኛ ወር በፈረንጆቹ አቈጣጠር ደንብ ከጥር ዠምሮ ሲቈጠር መጋቢት ሦስተኛ ወር መሆኑን በደንብ ያሳያል ።

ስለዚህ በሥፍራው ስንደርስ እንደምንመለከተው ጸሐፊው በአጻጻፉም በአቈጣጠሩም የውጭ አገር ትምህርት ያለው ይመስላል ። የቀሩት ግን ወርና ቀን ጠቅሰው ዓመተ ምሕረት የማይጠቅሱ ስላሉ የተጠቀሰውን ወርና ቀን ከየትኛው ዓመተ ምሕረት ጋር ለማያያዝ ይቸግራል ። የቀ[illegible]ንጉሡ የነገሡበትን በየአራት ዓመት የሚለዋወጠውን በዘመነ ማቴዎስ ፡ በዘመነ ሉቃስ ብለው ያልፉታል ።

በታሪክ አጻጻፍ ረገድ ባገሪቱ ላይ በዚያው በመጠኑ ብዙ የደረሰና የተደረገ የተፈጸመ ነገር እያለ በየመልኩ የታሪኩን ፡ የፍርዱን ፡ የአስተዳደሩን ፡ የጦርነቱን ታሪክ በአርእስትና በየምዕራፍ እየለዩ ሰፋ ባለ ሐተታ ለማቅረብ የጸሐፊነትና የአጻፊነት አቅም ስለጠፋ ከፖርቱጋል የመጡት የፖርቱጋል መልእክተኞች የመጡበትና ስድስት ዓመት ቆይተው የተመለሱበት ከፍ ያለ ጉዳይ በበኩሉ አልቫሬዝ በጻፈው ዓይነት እንኳን ቢቀር የርሱን ካስር እንዱን ያህል መጠን ያለው ጽሑፍ የኛዎቹ አላስቀሩም ። ፲፰ ዓመት የቆየው ብዙ ታላላቅ የጦር አለቆች ከጭፍሮቻ

(1) ሰባተኛው የሃሌ ሉያ ወር የሚለው ሃሌ ሉያ የዜማ ሁሉ መዠመሪያ የሆነውን እንደ መስከረም በመቁጠር መጋቢትን ነው ። አንዳንድ ጊዜ በሳብእ ወርኀ እም አውራኅ ኢትዮጵያ ይላል ።

(2) እንዳገራችን ወይም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አባባል ከክር. በፊት የነበረው ዘመን 5500 አሁን ዓፄ ገላውዴዎስ በ1533 ዓ. ም. ነግሠው ባሁኑ ጊዜ ከነገሡ 12 ዓመታት ያለው ተደምሮ 1544 ስለሚሆን ይህ ዓመት ከዓመተ ዓለም ጋር ሲደረብ 5500 + 1544 - 7044 ዓመት ይሆናል ።

(3) 1542 ዓ. ም. ያለው በስሕተት 2 ዓመት ያጐደለ ይመስላል ።

(4) በ1200 ዓመተ ሰማዕታት ያለው የ68 ዓመት ልዩነት ይታይበታል ፤ ምክንያቱም ዓመተ ሰማዕታት የሚባለው እንደ አው. ቀ. በ245 የተወለደው በ284 ዓ. ም. የነገሠውና እስከ 305 ዓ. ም. ገዝቶ በ313 ዓ. ም. የሞተው ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን ማሠቃየት የዠመረው በነገሠበት ዓመት በ284 (በኢት. 277 ዓ. ም.) ስለሆነ ይህ ዘመን ዓመተ ሰማዕታት የሚባለው የሚዠምርበት ስለሆነ 1268 ዓ. ም. መሆን አለበት ፤ ዓመተ ሰማዕታት አቆጣጠር ዘንድሮ (1965) 1689 ዓ. ም. ይሆናል ።

(5) [illegible]950 ዓመተ ተንባላት (የእስላሞች አቈጣጠር) የሚለው የ11 ዓመት ልዩነት ይታያል ። ሊሆን የሚገባው 961 ይመስላል ። ያፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ምዕ. 44 ።

ቸው ጋር የተላለቁበትን እነዚያን ያህል ገዳማትና አብያተ ክርስቲያን የተቃጠሉ በትን የግራኝ አህመድን የጦርነት ታሪክ ከግራኝ በኩል የነበረው ዓረብ ፋቂህ የጻ ፈውን ፋቡን ያህል የኛዎቹ ጽፈው ለዛሬው ትውልድ ያገለግል ዘንድ አልተዉም ።

የዓረብኛውን ብዙነት የኛን ቀንጽልነት ወይፊት በየምዕራፉ በሥፍራው ስን ደርስ በትክክል እንመለከታለን ። ይኸም ከፈረንጆቹ ብቻ ሳይሆን ከዓረቦቹም በሥ ልጣኔና ሥነ ጽሑፍ በማፋራትና አስፋፍቶ በመጻፍ ረገድ ዝቅ ብለን መገኘታች ንን ያስረዳል ።

የሥነ ጽሑፍና የታሪክ ነገር በተነሣ ቍጥር በዚህ ረገድ ላለብን ጉድለትና ችግር በዛሬ ጊዜ ፈላሻዩቱን ዮዲትንና ግራኝ አህመድን ያጋግሙን በአፐፊነት ኃላፊ አድርገናቸዋል ። ይኸውም ማለት ሁሉም በየመልኩ ተጽፎና ተዘጋጅቶ ሳለ ዮዲትና ግራኝ አህመድ ያነሡት ጦርነት ሁሉንም ወይም አብዛኛውን በቃጠሎና በዘረፋ አጠፋው ለማለት ነው ። ይኸን ብዙ ሰው ያምናል እኔም ራሴ የማምንበት ጊዜ ነበር ።

ነገር ግን የዛሬ ዘመን እውነትን ፈላጊ የሆነው አንባቢ በማያዳላ መንፈስና በእርጋታ የሥነ ጽሑፋችንን መጠን በዚያን ዘመን ያለውን የአባቶቻችን የጸሐፊ ነት አቅም አብዝተው በዚያን ዘመን ጠይ መንፈሳዊነት ማዘንበላቸውን ያጠናው እንደሆነ ከዚህ ጥርጣሬ ውጭ ሆኖ እውነተኛውን መንገድ ተረድቶ ሊጨብጠው ይችላል ። በፋላሻዩቱ ዘመንም ሆነ በግራኝ አህመድ ጊዜ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ብዙ መጻሕፍትና ንዋየ ቅድሳት መቃጠላ ቸውና መዘረፋቸው የማይከድ ነው ።

ISIC

ይሁን እንጂ በየዋሻው የተያበቀውን በየግል እጅ ያለውን ሁሉ ለማዳረስና ፈጽሞ ለማጥፋት ስለአልሆነለት እነሆ ቍጥራቸው የበረከተው ከግራኝ አህመድ በፊት የተተረጐሙትም የተደረሱትም ብዙው መንፈሳውያንና ተቶቶቹ ሥጋው ያን መጻሕፍት የግራኝን የወረራ ዘመን አልፈው ከጊዜያችን ደርሰዋል ። ዛሬ በምን መኛው ዓይነት ዝርዝር ይረቅ ታሪክ ያን ጊዜ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ እንደብዙው የመ ንፈሳዊው መጽሐፍ የሥጋዊውና የታሪኩም ጽሑፍ ተርፎ ከዘመናችን ሊደርስ በቻለ ነበር ። ነገር ግን ከላይ ባልነው ባቅምና በችሎት ማነስ አልተጻፈም ።

በዚህ ምክንያት መይምይማያውን ለኢትዮጵያ ታሪክ መሠረት ሆኖ እሁንም ወይፊትም የሚያገለግለው ፡

፩ኛ. ያው ባጭሩ አባቶቻችን ከመንፈሳዊ እንጋገር ጋር ያዘጋጁት ጽሑፍና በየጊዜው የተጻፈው ታሪክ ነገሥት ። ከዚያ ሲያልፍ ለጻድቃንና ለሰማዕታት በተጻ ፈው ገድል ውስጥ ባጋጣሚ ባንዳንድ ዓረፍተ ነገር ተጠቅሶ የሚገኘው ።

፪ኛ. ኢትዮጵያን እየጐበኙ የተመለሱ የውጭ አገር ጸሐፊዎች የጻፉትና ዓረ

በቹ እንማክረዝ ፤ እንኢዲን አህመድ የተጠቀ የጽሑፍ ቅርስ ነው ።

ለምሳሌ አንባቢ ወይፊት እንደሚረዳው ለእጁ ልብነ ድንግል ለመዝሙረ

ያው ዘመነ መንግሥታቸው ታሪክ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ የጻፈው ፣ ለግራኝ የወረራ

ታሪክ የዓረብ ፋቂህ (ሺሃብ ኤድ ዲን ቢን አብድል ቃድር) ፣ የሚትኢል ደ. ካስታን

ሆዞ ፤ የዮሐንስ ቤርሙዴዝ ፤ የፒዬር ቴሎዝ መጻሕፍት ናቸው ። እነዚህ የውጭ አገር ጸሐፎች ባይኖሩ ኖሮ የግራኝና የ፲፮ኛው መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ ሰማ ንያው በመቶ እንደተደፈነ ይቀር ነበር ለማለት ይቻላል ።

አንባቢም ጸሐፊም በዚህ ሁሉ መካከል አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር አለ። ከዚህ በላይ ያለውን ወደፊትም በየምዕራፉ ያለውን የጽሑፍ ጉድለት የምንመዝ ነው በዛሬው በሠለጠነው ዘመን አስተሳሰባችን ነው ። የዛሬ አእምሮአችን ብዙ ነገር በተለይ የፈረንጆችን እርምጃ ስለአስተዋለ የሥነ ጽሑፋቸውንም ምርት ብዛቱንና ዓይነቱን ጥሮአችን ስለሰማ ፣ ዓይናችንም ስለተመለከተ በዚያው መጠን ባገራ ችን በኩል ለምን አልተገኘም የሚሉ ጸጸትና ፍላጐት ይመጣብናል ። ነገር ግን እውነቱ ሲመዘን ያለ ሥፍራው ያለ አካባቢው ያለ አቅም ያለ ጊዜው የሚሆን ነገር ስለሌለ ያም ለዛሬ አእምሯችን ያነሰው ለዚያን ዘመን ሰዎች በቂ ሆኖ እንደሚገኝ የታወቀ ነው ። በዚያን ዘመን ከአውሮፖችና ከሥልጣኔያቸው ርቃ በዓረቦች ተከባ ለተቀመጠችው ኢትዮጵያ በጠቅላላው ሥልጣኔዋ በተለይ የሥነ ጽሑፏ ደረጃ ከፈረንጆቹም ከዓረቦቹም ዝቅ ቢል አስደናቂ አይደለም ። የትንሹን የኛን ያህል ከኛም ያነሰ የሥነ ጽሑፍ ቅርስ የሌላቸው ለሥነ ጽሑፍ መነሻም መድረሻም የሆነ ፊደልና አኀዝ መፍጠር ያቃታቸው የአፍሪካ ጐረቤቶች ስለአሉን በነዚያ ዓይን የኛ ሲታይ የሚያኮራና የሚያስመካ ሆኖ ይገኛል ። ከኛ ወደላይ ያለው ቢበልጠን ከበታቻችን ያለውን መብለጣችን የተረጋገጠ ስላሆን በዚሁ ተጽናንተን ዛሬ ጊዜ ውም ዕውቀቱም ባመቸበት ሰዓት በየመሥመሩ በሚበልጡን ለመድረስ መጣጣር አስመስጋኝ ነው ።

## ምዕራፍ ፰
## የአገር ሀብት ብዛት — የሕዝብ የኑሮ ደረጃ ማነስ

የኢትዮጵያ የሀብት ብዛት የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ማነስ ምን ጊዜም የታወቀ ነው ። ይኸውም ባለው ሀብት የመጠቀምን ዘዴ ከሚያውቁት አገሮች ካለመማር የተነሣ መሆኑን ለመገመት ምንም የሚያዳግት ነገር የለም ። የአገሩም ሀብት እህ ልና ከብት ብረታ ብረት ብቻ ሳይሆን ነገሥታቱ ካገር ላይ በግብር ከገባሮቻቸውና ከመኳንቶቻቸው ላይ በመታያ ምክንያት በሚያገኙት ወርቅ ሀብታምነታቸው በውጭ አገርና በጐረቤት አገሮች በግብፅና በዓረቦች ዘንድ የታወቀ ነው ።

ለንጉሠ ነገሥቱ በያመቱ የሚገባውን ግብር ከታሪክ ነገሥት ይልቅ ጽፈው ያቆዩን በኢትዮጵያ ብዙ ዘመን የተቀመጡት ከዚህ በፊት ስማቸውን የጠቀስነው የውጭ አገር ሰዎች ናቸው ።

ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ከጐጃም ለንጉሡ ላኤ ልብነ ድንግል (፲፭፻፲፪ - ፲፰ ዓ. ም. ላይ) የሚገባውን ግብር ለመሰብሰብ ታላቁ ቢትወደድ ሄዶ ሰብስቦ ለንጉሡ መጥቶ ሲያስረክብ እዚያው ነበርሁ ይልና ዝርዝሩን እንደዚህ ሲል አመልክቷል ።

፫ሺ. በቅሎዎች ፤

፫ሺ. ፈረሶች ፤

፫ሺ. የብልኮ ልብስ ፤

፴ሺ. ሌሎች ልብሶች ውድና ርካሾች ነገር ግን ዋጋቸው ፩ ወቄት የቀሩት ልብ ሶች ግን (ብልኮው) ከ፪ እስከ ፭ ወቄት ወርቅ (እያንዳንዳቸው ?) የሚያወጡ መሆና ቸውን ይገልጥና እነዚህ ሁሉ በሰልፍና በተራ በንጉሡ ፊት ሲያልፉ በመጨረሻ ፫ ሰዎች በአረንጓዴና በቀይ የገበታ ልብስ የተሸፈነ መሶብ ተሸክመው ማለፋቸውን እነሱም በመሶቡ ውስጥ የያዙት ባይታይም ጠይቆ እንደተረዳው ፴ሺ. ወቄት ወርቅ መሆኑን ይገልጻል ።

ስሞኑንም ባሕር ነጋሹና ትግሬ መኰንኑ ይዘው የመጡትን የሐር ልብስና ፈረስ በያይነቱ ሲያስረክቡ ፈረሶቹን ለማስረከብ የቀን ሞያ የሐሩን ልብስ ለማስከረብ ሌላ የቀን ሙያ መፍጀቱን ያመለክትና በሕይወቴ ይኸን ያህል የሐር ልብስ ብዛት አላየሁም ይላል (1) ።

ይኸው በኢትዮጵያ ፯ ዓመት (እ. አው. አቆ. ፲፭፻፳ - ፲፭፻፳፮ ዓ. ም.) የተ ቀመጠው አልቫሬዝ ሌላው ባገሪቱ ከ፴ ዓመት በላይ የተቀመጠው ያገሩ ልጅ ፔድሮ ዶ. ኮቪልሐእ «ባንዱ የዋሻ ግምጃ ቤት የታጀበው ወርቅ ዓለምን ሊገዛ ይች ላል» ብሎ እንዳጫወተው ገልጿል (2) ።

ወርቅ በብዛት የሚገኝባቸው የምዕራብና የደቡብ ኢትዮጵያ ባላባቶችና አገረ ገዥዎች ሳያቋርጡ ባመት ባመት የሚገብሩት ወርቅ በየጊዜው ማናቸውም ሰው በእጅ መንሻ ምክንያት የሚሰጠው ከቀረጣ ቀረጡ ጋር ሲደመር ከይኩኖ አምላክ ዠምሮ እስከዚህ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ (፩ሺ.፬፻፺፱ - ፩ሺ.፭፻፲፪ ዓ. ም.) (3) ነገሥታቱ በየጊዜው እየሰበሰቡ በማስቀመጥ ካደሉበት ጋር እየተጨ መረ ሲቀመጥ ከልክ ያለፈ እንደሚበረክት የታወቀ ስለሆነ እላይ ዶ. ኮቪልሐእ የተናገረው ከንቱ ቃለ አጋኖ ላይሆን ይችላል ። ዓለምን በወርቅ ለመግዛት ባይቻ ልም ካወቁበት ብዙ ታላላቅ በዓለም ያለ ነገር ሁሉ በወርቅና በገንዘብ ሊሠራበት ይችላል ። ዓለምም በወርቅ የሚገዛበት መንገዱ ብዙ ነው ።

በበኩሉ በኢትዮጵያ ፴፭ ዓመት ያህል የተቀመጠው ወደፊት በብዙ ምዕራፍ ላይ ስሙ ተጠቅሶ የሚገኘው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ወዳገሩ ሲመለስ በጻፈው መጽ ሐፉ ላይ ያንዱ የጉራጌ አውራጃ ባላባቶች ፲፪ ግልገል አንበሶች የሚመዝኑ (ወይም የሚያህሉ) ወርቆች ሌላም ዶልጋ አንበሳ ፣ አውራ ዶሮና ሴት ዶሮ የሚያካክሉ ወርቆች መገበራቸውንና እነዚህም ከመከበዳቸው የተነሣ ፳ ሰዎች ሊያነሡዋቸው እንደሚችሉ ! ወርቁ የተጣራ ጥሩ ወርቅ መሆኑን ከዚህም በቀር ፩ሺ. በሬ ብዙ የእን በሳና የነብር . . . . . ቆዳዎች መገበራቸውን ያመለክታል (4) ።

(1) Verdadeira informaçao. ምዕ. 128

(2) " " " 128

(3) 1512 እነአልቫሬጽ የመጡበት ነው

(4) Histoire du Christianisme-La Croze ገጽ 223

ይኸም ሁሉ ሐሰት ነው እንዳይባል ወደፊት እንደምናነበው አፄ ልብነ ድን ግል ራሳቸው ለፖርቱጋል ንጉሥ በጻፉት ደብዳቤ ላይ «ወርቅ በኔ ዘንድ እንደ ባሕር አሸዋ ነው» ብለው የጸሐፊዎቹን አነጋገር አጽድቀዋል ። ነገር ግን እንደ ዚህ እንደ አሸዋ በበረከተው ወርቅ ከውጭ አገር የጦር መሣሪያ ገዝተው ሳያስመ ጡበት ወታደር በብዛት እየመለመሉ ሳያሠለጥኑበት ወይም ለሕዝባቸው በቸርነት አድለው ወይም ላገር ጥቅም አውለው ሳይመሠገኑበት በመካከሉ የግራኝ ጦርነት ደርሶ ግራኝ አህመድ ከነጦሩ እርሳቸውንና የጦር አለቆቻቸውን አሸንፎ አገሪቱን የወረረ ጊዜ በሸዋና በቤተ አምሐራ በየሥፍራው የነበሩትን አብያተ መንግሥት ገዳማቱንና አብያተ ክርስቲያኑን አቃጥሎ በብዛት የደለበውን ወርቁንም የሐር ልብሱንም አግኝቶ ለራሱ ተጠቅሞ ወገኖቹን ጠቅሞ በተረፈው ወደ ዓረብ አገር እየላከ መሣሪያ በመግዛትና በተገዛው መሣሪያ ራሳቸውን እያጠቃ በመውጋት ተጠቀመበት ።

እነአትሮንስ ማርያም ፡ እነመካነ ሥላሴ ፡ እነአምባ ነገሥት (ግሼ) የተዘረፉ ጊዜ ከወርቁና ከሐሩ ልብስ ብዛት የተነሣ በዚያን ጊዜ ወርቅ መርከሱን ለማመል ከት የዓረቡ ጸሐፊ ከዘረዘረው በቀር የኛም ታሪክ ነገሥት «በዚያን ጊዜ ወርቅ የደን ጊያ ያህል የሐር ልብስም እንደዛፍ ቅጠል ሆነ» ሲል ያረጋገጠውን ወደፊት ከነዝር ዝሩ እናነባለን (1) ። ነገሩ ባንድ ወገን ንጉሠ ነገሥቱ ከነወገናቸው ሳይጠቀሙበት ጠላት እንደዚህ እስኪረከስበት ድረስ መጠቀሚያ ያስደንቃል ። በሌላ ወገን ግን አያስደንቅም ። ምክንያቱም በትምህርቱና በሥነ ጽሑፉ ደረጃ ላይ እንደተረዳነው በሠለጠኑት አገሮች እምሳል በንጉሡ መልክ የተቀረጸ ተዘዋዋሪ ገንዘብ በሌለበት ዘመን ወርቁ በወቄት እንኳን እየተለካ ወደውጭ አገር በመላክ መሣሪያ ካልተገዛ በት ፤ መምህራን እንዲያስተምሩ ካልተቀጠሩበት ፤ በየመሥመሩ ለየጉዳዩ ወጭ እየሆነ ባገር ላይ የርሻና የእንዱስትሪ ሥራ በዚያው በዘመኑ መጠን ከአልተቋቋመ በት ፤ ወይም ወርቁ ባገር ላይ ተበትኖ በአንጥረኛ እየተሠራ ሕዝብ ካላጌጠበት እን ደዚሁ የተቀመጠው ወርቅ እንዳሸዋ መበርከቱ በኋላም ውሎ አድሮ ጠላት ሲገባ ለጠላት የራት ክምር ሆኖ መቆየቱ የታወቀ ነው ።

በሰላሙ ጊዜ በወርቁ የቻሉትን ያህል የሚጠቀሙበት የተወሰኑ ናቸው ። እነ ርሱም ንጉሠ ነገሥቱ ከነቤተ ሰቡ ፤ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ናቸው ። እነዚህም የሚያጌጡት ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ የፈቀደላቸውና የሸለማቸው ናቸው ። ሌላው ተራው ሰው ትልቅም ሆኖ ወርቅ ቢኖረው ያለንጉሥ ፈቃድ ማጌጥ እንደማይችል ክልክልነቱ እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

ከወርቅ በቀር ባገር ውስጥ ያለው ሀብት አብዛኛው ያው ልዩ ልዩ አውራጃ ያፈራው እህል ፡ ከብት በያይነቱ ሞልቷል ። ነገር ግን የሥልጣኔያቸው ደረጃ እንኳን በዚህ ዘመን ካሉት ፈረንጆች ከአባቶቻቸው ክአከሱሞች እንኳን ዝቅ ያለ በመሆኑ

(1) "እሜሃ ኮነ ወርቅ ከመ እእባን ወልብሰ ሐሪር ከመ ቆጽል ፤" ታሪክ ነገሥት ባሉት ሬኔ ያሳተ መው ገጽ 331 - 332

ነገሥታቱ በስማቸውና በመልካቸው ያስቀረጹት የወርቅም የብርም ገንዘብ ስለሌላ ቸው መኳንንቱና ሕዝቡ የሚገበያዩት ከፍ ሲል በወርቅ ዝቅ ሲል ከብቱን እህሉን ልብሱን በማለዋወጥ ብቻ ነው ።

አል - ማክሪዚ ከባሌ ግዛት ያርሰው ከተመለሱ ነጋዴዎች እንደሰማው ሕዝቡ በበጐች ፤ በበሬ ፤ በላም ፤ በልብስ እየተለዋወጠ መገበያየቱን ይገልጻል ።

ይኸው አልቫሬጽ በመጽሐፉ ላይ በምዕራፍ ፳፰ ላይ በየአውራጃው ሲዘዋ ወር ያየውን እንደዚህ ሲል ይጽፋል ። «በመላ ኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ስለ ሌለ በገንዘብ ፈንታ የሚሠራበት ወርቅ ነው» ከዚያ ደግሞ በምዕራፍ ፳፱ ላይ «በየሳምንቱ የሚውል ገበያ አለ በገንዘብ በመሻሻጥ ፈንታ ዕቃ በዕቃ ይለዋወ ጣሉ . . . እህያ በላም ይለወጥና ግምቱ ሳይተካከል ሲቀር ያነሰው ፪ ወይም ፫ እን ጀራ ይከፍላል ። ሌላውንም በእንጀራ ፤ በጨርቅ ፤ በፈትል ፤ በሰማን ፤ በከርቤ ፤ በከ ብት በዶሮ ይለዋወጣሉ» ሲል ከመለከተ በኋላ ከዚያ ደግሞ እልፍ ብሎ በምዕራፍ ፶፫ ላይ እንደዚህ ይላል «በኢትዮጵያ ዋና የተወደደው የመገበያያ ገንዘብ . . . አሞሌ ጨው ነው . . . አሞሌው እየተፈለጠ ቁመቱ አንድ ስንዝር ተኩል ጐኑ የአ ራት ጣት ስፋት . . . . . ያለው ነው . . . . . በማሰድኑም አጠገብ (አሰብ ?) ፩፻፳ ወይም ፩፻፴ አሞሌ ጨው አንድ ድራህም ያወጣል ከማሰድኑ የአንድ ቀን መንገድ የራቀ እንደሆነ አምስት ወይም ስድስት አሞሌ ይቀንስና በመራቁ መጠን አሞ ሌው እየተወደደ በመሄድ በቤተ መንግሥት (ሸዋ ወይም ቤተ አምሐራ) ሲደርስ ያንድ ድራህም ዋጋ ስድስት ወይም ፯ አሞሌ ጨው ይሆናል ። . . . . .» ድራህም የጥንት የግሪክ የብር ገንዘብ ከብደቱ ፫ ግራም ከ፳፱ ሳንቲ ግራም ነው (1) ። ምናል ባት ድራህሙን የሚገበያዩበት የውጭ አገር ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም ።

ስለዚህ የአክሱም መንግሥት ከወደቀ ወዲህ በላስታም በሸዋም በጐንደርም እስከ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት ገንዘብ በመልካ ቸው ማስቀረጽንና ሕዝቡና ነጋዴው እንዲገበያዩበት ለማድረግ ሳይችሉ ቀርተው ከብት በከብት ፤ እህል በከብት ፤ እህል በልብስ እየተለዋወጠ በዚህ ላይ እንደገን ዘብ ተቆጥሮ መገበያያ የነበረው አሞሌው ጨው ነው ማለት ነው ። ይኸም ሩቅ ሳን ሄድ በጊዜያችን የማሪያ ቴሬዛ ብርና ዓፄ ምኒልክም በመልካቸው ያሠሩት ብር አላድ ሩብ መሐለቅ ቢሳ እያለ ሕዝቡ በየገበያው ፤ በየባላገሩ ከላይ በመጣው ዝቅ ተኛውን ሸቀጣሸቀጥ በአሞሌ ጨውና በጥይት ሲገበያይ ደርሰንበታል ።

ስለዚህ አክሱሞች በነአብርሃ ፤ በነካሌብ ጊዜ የነበራቸው ሥልጣኔ ከተከታዮ ቻቸው ከላስታ ከሸዋና ከጐንደር ነገሥታት የበለጠ እንደነበረ ከአክሱም መንግ ሥት ውድቀት ወዲህ ግን አገሪቱ በማናቸውም በገንዘብና በሐውልት ቅርጽ በንግ ድና በዕውቀት መስፋፋት በጦር ኃይልና ድርጅት ወደኋላ እንጂ ወደፊት አለመራ መዷን ይኸው ብቻ ያስረዳል ። በጐንደር ዘመነ መንግሥት (፲፯ - ፲፱ መቶ ዓመት) ነገሥታቱ ደስ ላሰኛቸው ይሰጡ የነበረውን የገንዘብ ዓይነት ዜና መዋዕላቸው

(2) Littré ገጽ 283

በብዙ ቦታ ሰቅለ ወርቅ ይለዋል ። ወደ ግብጽ ልከው ጳጳስ የሚያስመጡት ደግሞ ፩፻፺ ወቄት ወርቅ መሆኑን ያረጋግጣል (1) ።

ይሁን እንጂ ባገር ውስጥ ከወርቁና ከአሞሌው ጨው በቀር ሌላ ዋና ገንዘብ ከነቅንስናሹ ባይኖርም በዚሁ በወርቁ በአሞሌው አገሪቱ ባፈራችው ከብትና እህል እየተለዋወጡ ከኢትዮጵያ የሚወጣው ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው ሸቀጣ ሸቀጥ ብዙ ነው ። የወርቅ አንጥረኛ በቤተ መንግሥቱ እንደነበረ የምንረዳው ወደ ፊት እንደምናገኘው ከፖርቱጋል ጐበዛዝት ጋር እየታገለ ያሸነፈው ገብረ ማር ያም የሚባለው ዘሩ ዓረብ ሥራው አንጥረኛነት መሆኑን አልቫሬጽ ገልጾል ናል (2) ። በዚሁ ሰውዬ ውስጥም ሌሎች አንጥረኞች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው ። የሥራቸውን ዓይነት ለማወቅ በዚያ ዘመን ተሠርቶ በሙዚውማችን የተቀመጠ ዕቃ ስለሌለ የጥበቡን ዓይነትና ደረጃ ለማመዛዘን ችግር ነው ።

ይሁን እንጂ ከመካከለኛውና ከቅርቡ ምሥራቅ ፤ ከሕንድ ፤ ከፋርስ ፤ ከግብጽ ፤ ከዓረብ ፤ ከዘቢድ ፤ ከሐድራሞት ለቤተ መንግሥትና ለየአድባራቱ ፤ ለየገዳማቱ የሚሰጠው ልዩ ልዩ የሐርና የከፈይ ልብስ በያይነቱ በወርቅና በብር እየተጌጠ የሚሰጠው ስጋጃ ፤ ዣንጥላ . . . . . ብዙ ነው ። ሹመቱ እስከ ጊዜያችን የደረሰው ነጋድራስ በዚያን ጊዜ አጠራር ነጋድ አራስ የሚባለውን ሹመት ብዙ ጊዜ የውጭ አገር ሰዎችና ዓረቦች ይይዙት ነበር ። በገበዘ አክሱም መጽሐፍ ላይ አህመድ ነጋድ ራእስ ተብሎ ተጠቅሷል ። ስለዚህ በዚህ ዘመን የ፲፭፻፺ ኃላፊ እርሱ ይሆናል ። በተ ረፈ እንደ እርመናዊው ማቴዎስ ያለው የዓረብና የግሪክ የገቢናቫ ወይም የፋርስና የሕንድ ተወላጆች ሸቀጥ እያመላለሱ ቤተ መንግሥቱን ያከበሩ እነሱም የከበሩ እንደሚኖሩ አይጠረጠርም (3) ።

ነገሥታቱ ባጠገባቸው ያሉት አንዳንድ የውጭ አገር ተወላጆችና ፈረንጆች ማስረዳታቸው ሳይቀር በቤተ መንግሥቱም እንደ ታጋዩ ገብረ ማርያም ያሉ አንጥ ረኞች መኖራቸው ሲታወቅ እንደ አባቶቻቸው እንደአክሱሞች በመልካቸው ገን ዘብ ያላስቀረጹበት ለራሳቸውና ለሞቱት አባቶቻቸው ሐውልት ያልሠሩበት ምክ ንያት ምን ይሆን ? ።

የአክሱሞቹ ነገሥታት ከሰሎሞንና ከንግሥት ሳባ የሚወለዱ ናቸው እንደምን ለው እነዚህም ከይኩኖ አምላክ ገዥምረው በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥት ዙፋን ላይ የሚከታተሉት እሥራኤላውያን መሆናቸውን በየሥፍራው ያረጋገጡትን ጽሑ ፎች ባለፈው አንብበናል ። ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ በጻፉት ደብ ዳቤ ላይ «የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ልጅ ነገሥተ እሥራኤል» ብለዋል ። የነገሥታቱ ስም ዘርዓ ያዕቆብ ፤ ዳዊት ፤ ይስሐቅ ፤ ሚናስ እየተባሉ ሲጠሩ ይኸንኑ የእሥራኤል ተወላጅነታቸውን ያረጋግጣል ። በሃይማኖት ክርስቲያን ይሁኑ እንጂ በልማድ

(1) Annales Regum Iyasu II Et Iyoas - Guidi ገጽ 31. 33. 117 ። ሰቅለ ወርቅ ማለት ጥምዝ ወርቅ ማለት ነው

(2) አልቫሬጽ ምዕ. 87

(3) Liber Axum (29)

ዉድ እሥራኤል የሚሳቡበት ሁኔታ ብዙ ነው ። እንደ እሥራኤሎች ግዝረት አለ ፣ ዘርዓ ያዕቆብ ቅዳሜ እንዲከበር ያዘዙት እንደ ጸና ነው (1) ።

ስለዚህ በኦሪት «ሥዕልንም ምሳሌንም ከቶ ላንተ አታድርግ» ያለውን ለማክበር ይሆን ?። ይኸም ትእዛዝ በሐዲስ ተሽሯል እንዳይባል «ኦሪትን ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ብሎ ጌታ የተናገረው በማቴዎስ ወንጌል በግልጽ ይገኛል (2) ። ኦሪትን በማክበር ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ፈረንጅ የሚያደርገውን ሁሉ የኛዎቹ ማድረግ እንደማይወዱ ፈረንጅ የሚበላውንም እንደማይበሉ ግልጽ ነው ። ስለዚህ የገንዘቡንና የሐውልቱን ማሠራት ጉዳይ ባለመሠልጠን ብቻ ሳይሆን ሥራውን ራሱን የአረመኔና የአሕዛብ ሥራ ነው ብለው አውቀው ትተውት ይሆናል ብሎ ለመጠራጠር ይቻላል ።

ይኸም ጥርጥር እንጂ በቂ ማስረጃ አድርገን እምነታችንን በሙሉ አሳርፈን ልንተማመንበት አንችልም ። የወርቅን የብርንና የመዳብን ገንዘብ ከነቅንስናሹ በደንብ ቀርጾ መልክ ሰጥቶ ቍጥር ጨምሮ ሕዝብ በዚያ እንዲገበያይ ማድረግ ከሥልጣኔ አንዱ ክፍል ነው ።

ከአክሱሞች ውድቀት ወዲህ ግን በወይቦቹ መያዝ ከሠለጠኑት አገሮች ጋር ግንኙነት በመቋረጡ ምክንያት በዛጕዬዎቹም አሁንም በአማሮቹ ጊዜ ኢትዮጵያ በጠቅላላው ከሥልጣኔ ስለራቀች በደንጊያ ቅርጽ በጦር መሣሪያ ሥራ በሥነ ጽሑፍም ደረጃዋ ዝቅ ስለአለ ይኸም በመልክ በተቀረጸ ገንዘብ የመገበያየቱ ጉዳይ ከጠቅላላ ሥልጣኔ ጋር አብሮ የሚሄድ በመሆኑ በኦሪት ትእዛዝ ምክንያት ሳይሆን ጥቅሙን ባለመገንዘብና አሠራሩን ባለማወቅ ቀርቶ ይሆናል ።

የወላስሞች መደብ ከ፩ሺ፰፻፲፱ ዓ. ም. ወዲህ ከአዳል (ዳካር) ወደ ሐረር በዞረበትና ብዙ ዓረቦች ከማዶ ከዓረብ አገር እየመጡ ከአዳሎቹና ከሱማሌዎቹ ጋር በኖሩበት ሰዓት የሐረር ሕዝብ የመገበያያ ገንዘብ እንደነበራቸው ለማስረዳት አቡበከር ኢብን መሐመድ ሻንባል በአልዊ የሚባለው ዓዋ ገላውዴዎስ በሞቱበት ዓመት በሐረርጌ የተነሣውን የረሃብ ጽናት የእህሉን ውድነት ከተረከበት ላይ አንድ መለኪያ (ቁና) በቆሎ ፲፪ አሽራፍ አንድ መለኪያ (አሞሌ) ጨው ፳፭ አሽራፍ የበሬ ዋጋ ፫፻ አሽራፍ ከዚህም በላይ ሆነ ሲል ጠቅሷል (3) ።

ከአፄ ይኩኖ አምላክ ዠምሮ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ድረስ ምንም እንኳን አንድ አንድ ጊዜ የሽፍትነቱ ውጊያ ባይቀር ይፋትም ሐረርጌም በኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ሥር ሆኖ ሳለ ታላቁ መንግሥት የመገበያያ ገንዘብ ሳይኖረው የዝቅተኛው የሐረርጌ የሡልጣኖች ወይም የነኤሚር ኑር ነት በቀይ ባሕር ማዶ ከአሉት ከዘቢድ ዓረቦችና ቱርኮች ጋር የሥልጣኔ ግንኙነት ማዛት የመገበያያ ገንዘብ ሊኖረው የቻለው ይኸው ሐረርጌ በዘይላ ወደብ አማካይ

ISIC

(1) ኦሪት ዘፀዓት ምዕ. 20 ቍ. 4

(2) ማቴ. ምዕ. 5 ቍ. 17

(3) La letteratura etiopica-Enrico Cerulli. ገጽ 136

አድርጎ ሸቀጥ ለሸቀጥ እየተለዋወጠ ንግዱን በማስፋፋቱ ምክንያት ይሆናል ።

ወደፊትም ግራኝ አህመድ አፄ ልብነ ድንግልን አሸንፎ አገሪቱን ለመውረር የቻለው በሰውዬው ኃይለኛነትና ዘዴኛነት በዚህ በወይብ በኩል በመጣለት የጦር ወታደርና መሣሪያ ምክንያት መሆኑን ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

የተዘዋዋሪ ገንዘብ አለመኖር ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ባለው ዘመን መካከል ብቻ ሳይሆን ከአፄ ልብነ ድንግል ዘመን ቀጥሎ ባለው ዘመን ከ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ በነምሳዋ ንግሥት በማሪያ ቴሬዛ መልክ የተሠራው የብር ገንዘብ እስኪገባ ድረስ ከወቄት ወርቅና ከሰቅለ ወርቅ በቀር ሌላ ተዘዋዋሪ ገንዘብ ያለ አይመስልም ።

በ፲፯፻፺፩ ዓ. ም. የትግሬው ገዥ ራስ ወልደ ሥላሴ ለተፍጻሜተ መንግሥት ላይ ተክለ ጊዮርጊስ ፻፶ የወርቅ ዲናር እጅ መንሻ ማቅረባቸውን ታሪከ ነገሥቱ ይገልጻል (1) ። ይህ የወርቅ ዲናር እንደ ወቄት በመጠኑ የተቆራረጠ ንጹሕ ወርቅ ይሁን ፣ ወይም የትግሬው ገዥ ከምጥዋ ቱርኮችና ዓረቦች ጋር የሚገበያዩበት በደንብ የተቀረጸ የወርቅ ገንዘብ ይሁን በትክክል አይታወቅም ።

ስለዚህ ከአክሱሞች ውድቀት ወዲህ ከ፱ነኛው መቶ ዓ. ም. እስከ ፲፱ነኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ድረስ በአገሪቱ ከዚህ በፊት እንጻልነው መገበያያው ጨውና ንጹሕ ወርቅ ወይም ሸቀጥ በሸቀጥ ሆኖ ከኖረ በኋላ በ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ማሪያ ቴሬዛ በዓረብና በቱርክ ነጋዴዎች አማካኝነት በአገሪቱ ገብቶ መገበያያ ሆኖ ሲኖር ዳግማዊ ምኒልክ የባዕድ አገር ንግሥት መልክ ባለበት ገንዘብ መገበያየቱ ውርደት መሆኑ ተሰምቷቸው በመልካቸው ብር አሳድ ሩብ ተሙን አሠሩ ። ነገር ግን በዚህ በሽርፍራፊው ገንዘብ ሕዝቡ መጠቀሙ ባይቀርም ብሔራዊው የምኒልክ ብር ባዕዱን የማሪያ ቴሬዛን ብር መሻር አቅቶት እስከ ጊዜያችን ደርሷል ።

## ምዕራፍ ፱

## በዚህ ዘመን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ደረጃ

አገሪቱ ሰፊ ፣ የሰጧትን ዘር የምታበቅል ፣ አየሩ ለሰውነት የሚስማማ ፣ ደንና ዛፍ ወንዛ ወንዝና ሐይቆች የሞሉባት ወርቅ በብዛት የሚገኝባት ሀብታም አገር እንደ መሆኗ መጠን በዚህ ሀብት የመጠቀምን ትምህርት ከማጣት የተነሣ እንኳን በዚያ በራቀው ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን ዛሬም ቢሆን የድኅነት ኑሮ ከአገራችን ፈጽሞ አለመውጣቱ ለማንም የተሠወረ አይደለም ። መጠቀሙን ካላወቁበት የዕፅዋትና የዥረት የብርና የወርቅ ብዛት የመሬት ስፋት ራሱ ጠቃሚ ሆኖ የሕይወትን ደረጃ ሊያሻሽል አይችልም ። ሀብት እጥቅም ላይ የሚውለው ዛሬ እንደተረዳነው የወርቁም አገልጋይነት ፩ኛ ከመሬት በዘዴ ሲወጣ ፣ የወጣው በጥበብ ሲሠራ የተሠራው

(1) ታሪከ ነገሥት ገጽ 357

ወደ ውጭ አገር ተሸጦ በተገኘው ገንዘብ ባገር የሌለው ሸቀጣሸቀጥ ተገዝቶበት ወደ አገር ሲገባ ከሚወጣው ሀብትና ከሚገባው የሸቀጥ ጥቅም ሕዝብ በብዛት ተካፋይ ሲሆን የመንግሥቱ መሪዎች ሀብትን ለራሳቸው በማድለብ ፈንታ ለሕዝብ እንዲዳረስ ያደረጉ እንደሆነ ፤ ሕዝብ የሀብት ተካፋይ ሆኖ ለመሥራትም ለመነገድም ባገኘውም ገንዘብ እንደልቡ ለመኖር ለማጌጥና ለመልበስ ሙሉ ነፃነት ያገኘ እንደሆነ የኑሮው ደረጃ ተሻሽሎ ባይን ሊታይ ይቻላል ።

የኑሮው ደረጃ ተሻሽሏል የሚባለው ሕዝብ ለእግሩ ጫማ ፥ ለራሱ ባርኔጣ አድርጎ በደንብ ለብሶ ፥ በደንብ በልቶ የሚያድር ሕዝብ ነው ።

ከዚህ ተያይዞ ሲተረፈረፍ ከነዋሪው ሕዝብ ከሙቶ ሐያው ወይም ሰላሳው መሳፍንቱ ፤ መኳንንቱ ፥ ሹማምንቱ ፥ ሀብታም ገበሬዎችና ነጋዴዎች በመጠናቸው ከነሴቶቻቸው በአልማዝ በወርቅ በብር ሲያጌጡ የሐር ልብስ ሲለብሱ ከጥርብ ደንጊያ ወይም ከጥሩ እንጨት በተሠራ ቤት ሲኖሩ የቤቱ ውስጥ ወለሉ በሥጋጃ ሲሸፈን በቤት ውስጥ የሚተኙበት አልጋ የሚቀመጡበት ወንበር ያም ቢቀር በርጩማ ሲኖራቸው በቤት ውስጥ የሚገለገሉበት የመብልና የመጠጥ መሣሪያ በጥበብ የተሠራና የሚያማምር ሲሆን ነው ።

የዚህን ዓይነት የኑሮ ደረጃ በዚህ ዘመን የያዙ እነዚያው የአውሮፓ ሕዝቦች ናቸው ። ዝቅ ሲል ሕንዶች ፥ ቻይናዎች ፥ ፋርሶችና ቱርኮች ከዚያም ዝቅ ሲል ዓረቦች ናቸው ። የኛ ከነዚህ የሚቀጥል ነው ። ከኛ ደግሞ ጥቂቶቹ የአፍሪካ አገሮች ዝቅ ብለው ይገኛሉ ። ይህ ሁኔታ ዛሬ ስናነበው አዋራጅ መስሎ ቢሰማንም እውነቱን ክዶ በወግና በሥነ ሥርዓት ተለባብሶ ከእውነት በራቀ ስሜት መኩራቱም በአንደበት መግደርደሩም ፈጽሞ ከሞኝነት ይቆጠራል ።

ስለዚህ ወርቅ እንደ አሸዋ የሞላው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከነባለሥልጣኖቹ የሚኖሩበት የኑሮ ደረጃ የሚኖሩበት ቤት የሚለብሱት ልብስ የሚጠቀሙበት የቤት ዕቃ ከጠላት የሚዋጉበት የጦር መሣሪያ ከፈረንጆቹም ሌማቂው ነገዳችን ከፈለቀበት ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችም በጣም ያነሰ ነው ።

አል - ማክሪዚ የሚባለው የዓረብ ጸሐፊ ዓፄ ዳዊት (፲፫፻፷፬ - ፲፬፻፵) የላምጨንገራ እርጥቡን ሲበሉ ያያቸው ሰው እንዳጫወተው ሕዝቡም በእንጨት ተገድግዶ በአበት በተመረገ ቤት የሚኖር ፥ በመርፌ ተቀጣጥሎ ያልተሠፋ ተራ ልብሱን አገልድሞ የሚሄድ መሆኑን ፤ ንጉሡ የወታደሩን ቊጥር ስለማያውቀው በሚዘምትበት ጊዜ ባንድ ቦታ ዘማቹ ወታደር በነፍስ ወከፍ ደንጊያ መወርወሩን ፥ ከዘመቻ መልስ ተራፊው ወታደር ደንጊያውን በየራሱ ሲያነሣ የተረፈው ደንጊያ በጦርነት የሞቱትን የወታደሮቹን ቊጥር እንደሚያስረዳው ጽፏል (1) ።

እንደ አው. አቈ. ፲፭፻፳ ዓ. ም. ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ከዋናው አምባሳደር ከሮድሪግ ደ. ሊማ ጋር ከፖርቱጋል ንጉሥ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አፄ ልብነ ድንግል ተልከው ምጥዋ ደርሰው ከምጥዋ ወደ ባሕር ነጋሹ ከተማ ወደ ደባርዋ ሄደው ከባሕር ነጋሹ ከዶሪ ጋር የተገናኙ ጊዜ እንዲበሉ የቀረበላቸው ከስንደ

(1) Al Makirizi . . . . . . ገጽ 5 - 8 ። ዓፄ ዳዊት የነገሡበትና የሞቱበት ዘመን አጠራጣሪ ነው ፤ የገዙበትን አንዱ ጸሐፍ ፳፱ ዓመት ሲያደርገው ሌላው ፴፪ የቀረው ፴፬ ያደርገዋል ።

ጳቄት የተበለበሰ በሶ መሆኑን አልቫሬጽ ይጽፍና ያንን ደግሞ እንደዚህ ያለውን
መብል ሆዳችን አልለመደ.ውም ብለው ትተው ሲሄዱ ቢሉ የባሕር ነጋሹ እናት
«ሳይበሉ መሄድ ነውር ነው» ብላ ከመንገድ አስመልሳ ለመብል የስንዴ እንጀራ
ለመጠጥ በቀንድ ውስጥ ሆኖ የመጣ ጠጅ ቀርባላቸው ያንን በዋንጫ እየጠጡ
መመገባቸውን ይገልጻል (1) ።

ከዚያ ደግሞ እልፍ ብሎ «ባሕር ነጋሹ ማዕርጉ ከፍ ያለ ቢሆንም በአኗኗሩ
በጣም የደኸየ ነው ። ጉዳያችንን ለማስፈጸም ወደ ቤቱ በሄድን ቊጥር የምናገ
ኘው ጨርቅ በተሸፈነች ባንዲት ድንክ አልጋ ላይ ተቀምጦ ፤ ከጥጥ የተሠራ ሸማ
ለብሶ ነው ። ከኋላው ካለው ግድግዳ አጠገብ በተተከለ እንጨት ላይ አራት ሰይፍና
ጉራዴ ፣ መጻሕፍት ተንጠልጥለው ፤ ባለቤቱ ከርሱ ገርገባ በሰሌን ላይ ተቀምጣ
ይታያሉ ። በባሕር ነጋሹ ፊት ለፊት አራት ፈረሶች በደጅ አሉ ። ከነዚሁ አንዱ
ሁል ጊዜ እንደተጫነ ነው ። ባሕር ነጋሹን ሊገናኙና ደጅ ሊጠና የመጣው ሁሉ
እውጭ ተሰብስቦ ፀሐይ ሲሞቅ ይውላል ። ወደርሱ ከሚመጡት መኳንንት ዝቅ
ያሉት በትከሻቸው የበግ ለምድ በጣም ከፍ ያለ ማዕርግ ያላቸው የአንበሳና የነብር
የግምሻ ለምድ ይለብሳሉ» ይላል (2) ።

በባሕር ነጋሹ ቤት የታየው ሁኔታ ይነስ ይብዛ በሌሎቹ የኢትዮጵያ መሳፍን
ትና መኳንንት ቤት የሚታይ ነው ። ከተቆላ የስንዴ ዱቄት በሶ አቀረቡልን ያለው
እንደአጋጣሚ የእንጀራ መጠን በማነሱ ይሆናል እንጂ እንደዛሬ በዚያን ጊዜም እን
ጀራ በወጥ እንደሚበላ የታወቀ ነው ። እነ አልቫሬጽ ከአውራጃ ወደ አውራጃ ተላ
ልፈው ሸዋ በገቡና ፮ ዓመት በኢትዮጵያ በቆዩበት ጊዜ የሚፋጅ በርበሬ የበዛ
በት የዶሮ ፣ የበግ ፣ የበሬ ወጥ ከእንጀራ ጋር ቀርቦልን በላን እያለ በሌላ ዘንድ ተር
ኳል (3) ። ወደ ቤተ መንግሥቱ ከደረሱ በኋላ እስከ ቅርብ ጊዜ ለውጭ አገርም ላገ
ርም ውስጥ እንግዳ እንደሚደረገው ነጫጭ እንጀራ በወጥ ፍሪዳና ጠጅ እስከ ሠፈ
ራቸው ድረስ ይላክላቸው እንደነበረ ገልጿል ።

ሸዋ ለንብተው በቤተ አምሐራ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሥራው
አልቆ ታቦቱ የሚገባበትን በዓል ለማክበር ንጉሥ ነገሥቱን ተከትለው በሄዱ ጊዜ
የሚያጅባቸውን የሰውና የከብት ብዛት በተረከበት ምዕራፍ ላይ በጉዞ ጊዜ ንጉሥ
ነገሥቱ ፶ሺ አንዳንድ ጊዜ ፻ሺ በቅሎኛ እንደሚያጅባቸው እግረኛው ግን ቊጥሩ
በጣም የበረከተ መሆኑን ይገልጽና ከአጃቢው ካሥር አንዱ በአለባበሱ የተሻለ
በሁኔታው ነቃ ያለ መሆኑን ከአሥሩ ዘጠኙ ግን ወንድና ሴት ግማሾቹ ጨርቃጨ
ርቅ ግማሾቹ ቆዳ የለበሱ ተራ ሰዎች መሆናቸውን በጉዞ ጊዜ ተራዎቹ ሰዎች ያደሩ
በትን ጎጆ እንደተከደነ ትቀለው (ሁለተኛ ላለመሥራት) ተሸክመው እንደሚጓዙ
ታላላቆቹ መሳፍንትና መኳንንት ግን እያንዳንዳቸው የሚበቃቸውን ያህል ማለ

(1) Verdadeira informacao በነአቶ ግርማ ትርጉም ምዕ. 18 - 19

(2) " " በነአቶ ግርማ ትርጉም ምዕ. 62 - 63

(3) ምዕ. 101 ገጽ 257

ፊያ ድንኳንና ቍጥራቸው የበረከተ ተከታይ ሰውና የቍንት አጋሠሥ እንዳላቸው ያመለክታል (1) ።

ከንጉሡ ንጉሠ ተና ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስ ከእቴጌ ዩቲ ከሰብለ ወንጌል ወይም ከንጉሡ እናት ከእቴጌ ናዖድ ሞገሳ በቀር የቀሩት የመሳፍንትና የመኳንንት የቤት ውስጥ ኑሮ በባሕር ነጋሽ ቤት ካየነው ኑሮ የተሻለ ሊሆን አይችልም ። ባሕር ነጋሽ በዚህ ጊዜ ይሪ የሚባለው የንጉሡ ንጉሠ ተ አጐት የእቴጌ ናዖድ ሞገሳ ወንድም ስለሆነ ቍጥሩ ከንጉሣዊ ቤተሰብ ውስጥ ነው ። የሚቀመጥበት የደባሩዋ ከተማ አንድ አንድ ጊዜ ግብጾችና ቱርኮች ቢቀመጡትም የምጥዋ ወደብ የዳህላቅ ደሴቶች ሁሉ በርሱው ቍጥጥር ውስጥ ስለሆኑ የርሱ ግዛት ከሌሎቹ ግዛቶች የሥል ጣኑ ሥራ የሚታይበት ጥሩ ጥሩ ሸቀጥ የሚገባበት ብዙ ሀብት የሚገኝበት ስለሆነ የርሱ የኑሮ ደረጃ ከሌሎቹ የተሻለ ሊሆን በተገባ ነበር ።

ነገር ግን የኑሮውን የደረጃ መጠን ስንመለከት መሳፍንቱና መኳንንቱ ምንም ሀብት ቢያበዙ ግዛታቸው ሰፊ አውራጃ ቢሆን የሹመት ማዕርጋቸው ከፍ ቢል ከውጭ አገር ኑሮ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ስለአላደረጉና የንዚያን የልብስ ፥ የቤት መሣሪያ በማየትና ዋጋ በመስጠት ባገራቸው በማስገባት ኑሮአቸውን ስለአ ላሻሻሉ ያንኑ የተለመደውን ነዋሪውን ልብስና መሣሪያ ብቻ እያደረገው በዚያው ተደስተው ይኖራሉ ማለት ነው ። በዚህም ምክንያት ለኛ ከንግሥት ዘውዲቱ ዘመን ገርምሮ ኢትዮጵያን ለምናውቃት ግር ሊለን አይችልም ።

በዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን ብዙ ሀብት ያላቸው ማዕርጋቸው በቤተ መንግሥቱ ከፍ ያለው መኳንንትና መሳፍንት በሀብታቸው አሁን በምናውቀው ዓይነት ለመጠቀም ነዋሪው ልማድ ስላገዳቸው እንደ ባሕር ነጋሽ ሲታመሙ የማይታከሙ ፥ ከመኪና በቅሎን ፥ ከሱፍ ሐር ቅ መሐሙዲን ፥ ከሱፍ ካቦርት በርኖስን ከዚያ ከፍ ሲል ካባን የሚመርጡ ነበሩ ። ከእ ነዚህም ውስጥ እስከ ኢጣሊያ መምጣት ድረስ የዘለቁ አሉ ።

ይህ ኑሮን የማሻሻል ጉዳይ ባንድ ወገን በመሠረቱ ከለመማርና የውጭን አገር ኑሮ ካለማየት የተነሣ ቢሆንም ለልብሱና ላለባበሱም ዋጋ የመስጠት ችሎት ሊጎድል ይችላል ። ወይም በፍጹም አለመፈለግና እንዲያውም መናቅ አለ ። በዚህ ጉሡ ፊት ባልተፈቀደ ወርቅና ብር አጊጠው ተሸቀርቅረው ለመታየት ቤታቸውን በ ምንም ቢችሉ በጥሩ ጥሩ መሣሪያና ሥጋጃ ለማስጌጥ መብትና ነፃነት አልነበራቸ ውም ።

በዚህ ዘመን ታላላቆቹ መኳንንት እንኳን በተለይ በንጉሥ ፊት ባዳዲስ ልብስ አጊጦ ተሸቀርቅሮ መልካም ልብስ ለብሶ መገኘት ይቅርና የተለመደውንም መከከ ለኛ ልብስ በንጉሡ ፊት ለብሶ መታየት ክልክል መሆኑን በኢትዮጵያ ብዙ ዘመን የኖሩት አልቫሬጽና ቤርሙዴዝ በየመጽሐፋቸው ይገልጻሉ ።

(1) ምዕ. 216

ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ትልቁ ቢትወደድ ከጐጃም የንጉሡን ግብር ሰብስቦ ከመጣ በኋላ ለማስረከብ ከንጉሠ ነገሥቱ በተገናኘበት ሰዓት ከወገቡ በላይ ራቁቱን እንደነበረ ይገልጻል (1) ።

የፖርቱጋሎችን ርዳታ ከፖርቱጋልና ከሕንድ አጣድፎ ይዞ የመጣው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በኢትዮጵያ ፴፭ ዓመት ከተቀመጠ በኋላ ወደ አገሩ ሲመለስ በጻፈው መጽሐፍ ላይ «በዳሞት ጕን ያለ ብዙ ሀብት የሞላበት የኩሽ መስፍን (2) ሸፍቶ ቆይቶ ሳለ በኋላ ታርቆ ሲገባ ላዬ ገላውዴዎስ የሚቀርብ ብዙ ወርቅና ከብት ይዞ በገባበት ቀን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀረብ ሲል ከፈረሱ ወርዶ የለበሰውን መልካም ልብስ አውልቆ ለአሽከሩ ሰጥቶ በዚያ ፋንታ የተዋረደ ልብስ ለብሶ ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኘ» ሲል ይገልጻል (3) ።

ከመንግሥት ሹማምንትና መኳንንት የባሰ የመንግሥት አሽከር ባልሆኑት ባላገርና ነጋዴ ዘንድ ያለው ሁናቴ በዛሬ መንፈስ ሲገመት ፍጹም አሳዛኝ ነበር ። በቅርቡ በነአፄ ዮሐንስ በነአፄ ምኒልክ ዘመን ለመንግሥት አድሮ ወይም ንጉሥን ደጅ ጠንቶ የሹመትና የማዕርግ ስም ካልተሰጠውና ካልተሸለመ በቀር እህል አምርቶ ከብት አርብቶ ወይም ነግዶ ሀብት ቢያገኝ ባገኘው ሀብቱ የፈቀደውን ማድረግ አይችልም ነበር ። የቀረው ቢቀር ለብቻው በቤተ ሰቡ ውስጥ ኮርማ አርዶ መብላት ጠጅ አስጠጅቶ መጠጣት ፣ ጠፍር አልጋ ላይ መተኛት ፣ በጥልፍ ዕቃ በተሜነች በቅሎ መቀመጥ ፀሐይ ወይም ዝናም እንዳይመ[illegible]ጥላ እንዳይዝ በአዋጅ ክልክል ነበር ። ይኸንንም አዋጅ የጣሰ ይወረስ ነበር ። ጌታሁን ግሜ የሚባል የደጋ መቄት ተወላጅ በእርሻ ፣ በከብት ርባታ ፣ በንብ ማርባት የከበረ የማርያም ለት ፍሪዳ አርዶ ጠጅ አስጠምቆ ካህናቱን በመጋበዙ ጕረቤቱ ከሶ ዓፄ ዮሐንስ (፩ኛ) ላይ አቅርቦት መኳንንቱ ሁሉ ይቀጣ ካሉ በኋላ ዓፄ ዮሐንስ ምሕረት እንዳደረጉለት አቶ መዓዛ ለማ በጻፉት ማስታወሻ አስገንዝበውናል (4) ።

ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ አውቆ በሥልጣኑና በፈቃዱ እየመጠነ ከአልቸረ በቀር የተገኘው የወርቅና በከበረ ደንጊያ የተሠራ ማናቸውም የልብስና የመሣሪያ ጌጣጌጥ ሁሉ አብዛኛው ጊዜ ገቢነቱ ለቤተ መንግሥት አለዚያም ለቤተ ክህነት ስለሆነ አሁን ወደፊት ግራኝ አህመድ እየዘረፈ ለሹማምንቱ በማደል ወደ ዓረብ አገር እየላከ የጦር መሣሪያ እየገዛ ወታደር እየመለመለ የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ ሕዝብ እስከ አጠቃበት ድረስ የሀብታሟ የኢትዮጵያ የወርቅ ሀብት ከአፄ ይኵኖ አምላክ ዠምሮ በየቤተ መንግሥቱና በየገዳማቱ ዶልቦ በመቀመጥ ሕዝቡም መኳንንቱም ሳያጌጡበት የሕይወታቸውን ኑሮ ሳያሻሽሉበት መንግሥቱ ከጠላቱ የሚከላከልበት ዘመናዊ መሣሪያ ሳይገዛበት እንደዚሁ ኖረ ።

(1) Verdadeira informacao-F-Alvarez ምዕ. 118

(2) የወለጋውን ይሆን ወይስ የሸገሌን አለዚያም የጋፋትን ባላባት ?

(3) Histoire du christianisme d'Ethiopie-La Croze- ገጽ 230 - 235

(4) ሀብትና ጤንነት — መዓዛ ለማ — ገጽ 9 - 14

የመሳፍንቱና የመኳንንቱ የሕዝቡ ኑሮና አለባበስ ከላይ በትንሹ በተመለከተው ዓይነት ሲሆን የንጉሠ ነገሥቱን የዚህን ዘመን አለባበስና የቤት ውስጥ ኑሮ ይኸው አልቫሬዝ ወደፊት በምናነበው ምዕራፍ ውስጥ ምልክቱን ይሰጠናል ። በቤተ መንግሥቱ በደረሱ ጊዜ የከልካዩን ግራና ቀኝ መበርከት የቆሙትን የሸማምንት ብዛት ከተረከ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት አዳራሽ በገቡ ጊዜ ግድግዳዎች ጌጣጌጥ በአላቸው መጋረጃዎች ታጥረው በወለሉ ላይ ሰፋፊ ሥጋጃዎች ተንጥፈው እንደነበሩ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በራሳቸው ላይ ከወገቡ በላይ በወርቅ ከወገቡ በታች በብር የተሠራ ዘውድ ደፍተው በእጃቸው የብር መስቀል ይዘው እንደነበረ አፋቸውን ከነአፍንጫቸው በሰማያዊ ሐር ተሸፍነው እጅጌያቸው ሰፋፊ የሆነ የሐር ሸሚዞች (እጀጠባብ) ለብሰው በዚያ ላይ ካባ ደርበው ከታች ግን በሙሉ ስለ ተሸፈኑ እግራቸው የማይታይ እንደነበረ ያመለክታል (1) ።

ከአውራጃ ወደ አውራጃ ሲጓዙ ዘውድ ጭነው በበቅሎ ላይ ተቀምጠው በኋላ ከቀኙና ከግራ ቁመቱ ወደ ላይ ከፍ ያለ ቀይ ቀለም ባለው መጋረጃ ውስጥ ተጋርደው እንደሚሄዱ ፡ ሁለት የልፍኝ አሽከሮች የበቅሎዋን ልጓሟን ሁለት ሌሎች ጋማዋን ሌሎች ደግሞ ሽንጧን (ዳሌዋን) ግራ ቀኝ ደግፈው ከመጋረጃው ውስጥ ሆነው እያጀቡ እንደሚሄዱ ስለሚጽፍ (2) ከወደፊት ያለው መጋረጃ የቀረበት ምክንያት ለመራመድ ብቻ እንዳይከለክል ነው ማለት ነው ።

ISJC

የአጀቢው ብዛት እንኳን በዚያን ዘመን ይሁን ቢያሰኝ በረዥም ጉዞ ጊዜ ይኸን የመሰለ ግርዶሽ መቅረቱ ባልከፋ ። በዛሬ እስተያየታችንም የግርዶሹ መቅረት ምንም ያህል ንጉሠ ነገሥታዊ ክብራቸውን ሊቀንስ ባልቻለ ። ይኸም ከዚያው ልማድን ከአለማሻሻል የተነሣ ነው ።

የሆነ ሆኖ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከአፄ ልብነ ድንግል ጊዜ ዠምሮ ምንም ያህል መሻሻል ሳያገኝ በ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ዳግማዊ ምኒልክ የአገሪቱን በር ለአውሮፓ ሥልጣኔ በመጠኑ ሲከፍቱ የመጀመሪያው ትምህርት ቤትና ሆስፒታል በአዲስ አበባ ሲከፈት የምድር ባቡርና የስልክ መስመር ሲዘረጋ ሚኒስትሮች ለየሥራው ሲደለደሉ የፈረንጅ ቁጥር ባገር ተቀማጩም ተመላላሹም እየበረከተ ሲሄድ ለፈረንጅ ለአኗኗሩ ለአበላሉና ለአለባበሱ እንኳን ቢቆይ ለዕውቀቱና ለሥራው ዋጋ መስጠትና ፈረንጅን የማክበር መንፈስ በመጠኑ ተጸነሰ ። የርሳቸው ዘመን አልፎ የንግሥት ዘውዲቱና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሲተካ የሥራው ድቅን የትምህርት ቤቱ ቁጥር እየበረከተ ሄደ ። ይኸውም ሆኖ አዲሱን የፈረንጅ ትምህርት ከነልብሱ ከነመብሉ ከነኑሮው የሚጠሉት ልጆቻቸውንም የሚያስጠሉትን እናስታውሳለን ። የነርሱ አሳብ እንደ ጃፓን እውቀቱን እንማር በልብስና በአበባል ወይም በአኗኗር የኛኑ እንልቀቅ ሳይሆን ትምህርቱን ራሱን ጭምር ይጠሉት ነበር ።

(1) ምዕራፍ 83
(2) ምዕራፍ 230

ቢሆንም አዲሱ ትምህርትና ኑሮ ከሥር ቢያንስ ቢያንስ ከሁለት ትውልድ ሳይያያዝ ስለመጣ የጠቅላላው ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ከጥንቱ ተለይቶ የፈረንጆችን የኑሮ ደረጃ መሥመር ሳይከተል በመካከል ኢጣሊያ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ወደ ኢትዮጵያ ገባ ። አገሪቱን በያዘበት በ፭ ዓመታት ውስጥ ለራሱ የአገር ተወላጆች በየአውራጃው የሠራቸው ልዩ ልዩ ሕንፃዎች ከነፃነት በኋላ ሳገለገሉ ሰዎች በታደለ ጊዜ እነዚህ ያገለገሉ ሰዎች የኑሮአቸው ደረጃ ዝቅ ከማለቱ የተነሣ ቀድሞ የነበሩበት የሣር ክዳንና በጭቃ የተመረገ የቤት ሕይወት ሳሁኑ በብዙ ክፍል ለተለያየው ሕንፃ እንግዳ ከመሆን የተነሣ ባንዳንድ ሳሎኖች በቅሎዎች ከመታሠር ደርሰው መታጠቢያ ቤቶችም ወደ መኝታ ቤትነት ተለውጠዋል ። ብዙ የመዝጊያና የመስኮት እንጨቶች በባላገር እጅ እየተፈላለጡ መብል ማብሰያ ሆነዋል ።

ልጃቸው በአርበኝነት የሞተ አንዲት ሴት የቀድሞ የሣር ክዳን ቤታቸውን አፈራርሶ ጣሊያን አንድ መጠነኛ የሕንፃ ቤት በላዩ ላይ ሠርቶ ስለሄደ ስለሟቹ ልጃቸው ውለታ ያ ሕንፃ ቤት ለሴትዮዋ ተሰጠና ገቡ ። በገቡ ማግሥት ሴትዮዋ በዶማ የሲሚንቶውን ወለል መቆፈር ዠመሩ ። ከጐረቤት አንድ ሰው ብቅ ብሎ «ምን ይሠራሉ» ቢላቸው «የቤቴን ወለል ጠላት በሲሚንቶ አድርቆ ሠርቶት ገንቦና እንስራ አያስቀምጥ ዕቃ ከእጅ ቢያመልጥና ቢወድቅ ሳይሰበር አይነሣ ስለዚህ ጣሊያን አበላሽቶብኝ የሄደውን የቤቴን ውስጥ እሠራለሁ» አሉ ይባላል ።

በ'ነህ ሴትዮ አስተያየት የቅርቡን የሩቁን ላይ ዠምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ ያለውን ጠቅላላ ስሜት እንረዳለን ።

ISIC

አንድ ሕዝብ ከእያት ከቅድም እያት ተያይዞ ያልመጣውን ሥልጣኔና ኑሮ ባንድ ጊዜ ተቀብሎ ዋጋ ሊሰጠውና ሊጠቀምበት አይችልም ። በግድ እንደ ሴትዮዋ ቢደርስበትም ግንጥል ጌጥና የማይዋሐድ ሆኖ ሰውዬውና ቤቱ ከነመሣሪያው ሳይጣጣሙ ሳይገጣጠሙ ይቀራሉ ።

ስለዚህ በተለይ በዚህ አፄ ልብነ ድንግልና ግራኝ አህመድ በተዋጉበት ዘመን ያለው ሕዝብ የኑሮአቸው ደረጃ ከፍ ካለው ከፈረንጆች ሃይማኖትና ዕውቀት የራሱን ሃይማኖትና ዕውቀት ከፈረንጅ ግጥምና ዜማ የራሱን ቅኔና ዜማ ከፈረንጅ የሕንፃ ቤት የራሱን ደሳሳ ጎጆ ከፈረንጅ ልብስና መብል የራሱን ለዚያው ላለበትና ለለመደው የኑሮ ደረጃ ተስማሚና ተመጣጣኝ የሆነውን መብልና ልብስ ይመርጣል ።

ነገር ግን በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የተወጠነው የፈረንጆች ሥልጣኔ ዛሬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ከመስፋፋት ላይ ሲገኝ ሕዝቡ በተለይ ከፍተኛው ክፍል ዘመን ያመጣውን ሥልጣኔ በግድም በውድም በመከተል በሚችለው መጠን ከሣር ክዳን ቤት እየወጣ የሕንፃ ቤት እያሠራ መቀመጥ ፤ ከኩታ ከእጀ ጠባብና ከበርኖስ ተለይቶ የሱፍ የፈረንጅ ልብስ መልበስ ፤ በመሬት ተቀምጦ ከወስከንባይና ከመሶብ ቆርሶ በእጅ በመመገብ ፈንታ በወንበር ተቀምጦ ከጠረጴዛና ከሣህን ላይ በሹካና በቢላዋ መብላት ዠመረ ። በበቅሎና በፈረስ እግር መንኰራኩሮች (አውቶሞቢሎች) ተተኩ ፤ ቀድሞ ይናቅ ይጠላ የነበረውን ትምህርት ወጣቶች በትጋት ያባሩት ዠመር ።

ያንደኛውን ዘመን መንፈስ ለሌላው ዘመን ወደ ኋላ ተመልሶ ማዛወርና መስጠት አይቻልም እንጂ የዚህ የአሁኑ የሥልጣኔ ናፍቆት መንፈስ ባዬ ልብነ ድንግል ዘመን ዋዜማ ለነበሩት ባለሥልጣናች አድሮ ቢሆን የግራኝ ወረራ እንደዚህ በቀላሉ ባልተቃናለት ነበር ። እርሱ ከዘቢድ ባሻዎች በገዛቸው ነፍጥና መድፎች ሲዋጋ የኛዎቹ በጦርና በጕራዴ በመከላከል ፈንታ መድፉን በመድፍ ነፍጡን በነፍጥ እየወጉ በመለሱት ነበር ። በሁለቱም ወገን ያለው ሕዝብ የተዋጊነት መንፈሱ የጀግንነቱ መጠን ተመሳሳይ ስለሆነ በቆየ ድርጅትና በሀብት በሠራዊት ብዛት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ስለሚበልጥ የድል ዋንጫ ከዓፄ ልብነ ድንግልና ከመኳንንቶቻቸው እጅ ባልወጣ ነበር ።

በመዠመሪያው የጦርነት ወቅት ግራኝ በነፍጥና በመድፍ መጠቀሙን የርሱ ጸሐፊ ዓረብ ፋቂህም የኛም ታሪክ ነገሥት አያወሳም ። የመዠመሪያዎቹ ጦርነቶች በኛ ዘንድ ንቀት በነበረበት መንፈስ ሲያዝ በርሱ በኩል ትጋትን ፣ ጥካኔን ፣ ተንኮልን ጨብጦ ስለተነሣ ሊቀናው ቻለ ። ከቀናው በኋላ የኛዎቹ እድልበው ባስቀመጡትና አግኝቶ በዘረፈው ሀብት ከግዶ ከዓረብ አገር ነፍጥና መድፍ እየገዛ አምጥቶ በሚዋጋበት ጊዜ የኛዎቹ እምርረው ጨክነው ቢዋጉም ትርፉ ሕዝብ ማስጨረስ ብቻ ሆነ ። የዚህ ዓይነቱ አሳዛኝ ጦርነት ወደፊት በየምዕራፉ ይገኛል ።

ISIC

# ፪ኛ ክፍል
# የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ግንኙነት

## ምዕራፍ ፲

### በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል ያለው የሃይማኖትና የሥልጣኔ ልዩነት - የፖርቱጋል ኃያልነት በኢትዮጵያ ስለመሰማቱ ።

በግራኝ ጦርነት ዋዜማ ባለው የአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ለዝምድና በሚፈላለጉት በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል የዘርና የሃይማኖት ልዩነት መኖሩ የታወቀ ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራውና ትግሬው ጉራጌው አደሬው ሴማዊ ከደቡብ ዓረብ የፈለቀ ጋላው ምንም ገና በዚህ ዘመን ወደ ላይ በብዛት ባይመሠረት ከአፍ ሪካ ቀንድ የመጣ የካም ወገን ፤ ዙሽ ሻንቅላው ካገር በቀል ሆኖ ከደቡብና ከምዕ ራብ ክፍል እየመጣ የተጨማመረ ሲሆን የፖርቱጋል ሕዝብ ሴልቶ ኢቤሪክ የሚ ባሉ የሂንዶ - ኤውሮፖ ወገን ሆኖ ሊዙታኒ ይባላል ። ሁለቱ ሕዝብ በቀለም ፤ በቋ ንቋ ፤ በአኗኗር ልማድ በሥልጣኔ በአገሩና በሥፍራው መራራቅ መጠን የተለያዩ ናቸው ።

ISIC

በሃይማኖት ረገድ ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ባለው ጊዜ ሁለቱም ከአ ረመኔነት አልዘለሉም ። የኢትዮጵያ አንዱ ክፍል የሙሴን ሕግና ልማድ እሪትን የተቀበለ ቢመስልም በጠቅላላው እስካሁን የተገኘው ማስረጃ ነገሥታቱ እነዲዛና የጨረቃን አምላክ ማሕረምን አምላኪ በመሆናቸው ከአረመኔነት አልወጡም ።

በኋላ ኢትዮጵያ ክርስትናን ከእስክንድርያ ፖርቱጋል ከሮማ ቤተ ክርስቲያን ስለተቀበሉ የፖርቱጋል ሕዝብ ካቶሊክ ሆኖ ጳጳሱን ከመንበረ ጴጥሮስ ከሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሲቀበል የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥት ሃይማኖት ተዋ ሕዶ ስለሆነ ጳጳሱን ከመንበረ ማርቆስ ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ ይቀበላል ። አሁን ኢትዮጵያን በደቡብ የእስላሞች ኃይለኛ እንቅስቃሴ እያሠጋት ፖርቱጋልንም የግ ዛትና የንግድ ማስፋት ምኞት ጥቅምና ፖሊቲካ አቀራረባቸው እንጂ ተዋሕዶና ካቶሊክ በክርስቶስ ባሕርይ ምክንያት ከተለያዩበት ከኬልቄዶን ጉባዔ (እ.ኤ.ቀ. ፬፻፶፩ ዓ. ም.) ወዲህ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የማይታለፍ ጠብና ባላጋራነት እንደነበረ ግልጽ ነው ።

በዚህ ምክንያት ተላልከው በስንት ድካም ተቀራርበው ከተዛመዱ ወዲህ በዝምድናውም ይሁን በጥቅሙም ሳቢያ ፬፻ የፖርቱጋል ተወላጆች መጥተው ለኢ ትዮጵያ ደማቸውን ካፈሰሱ በኋላ ቀጥተኛውን የሁለቱን አገሮች ዝምድና እነቢር ሙዴዝ ፤ እነአንድሬያ ኦቪዮዶ ኢትዮጵያ ካቶሊክ ትሁን ሲሉ የኛዎቹ አንሆንም በማለት የተነሣውን ጠብና ክርክር ከሃይማኖቱ ልዩነት ጋር በጦርነቱ መጨረሻ ላይ ባዬ ገላውዴዎስ ዘመን በሰፊው እናነባለን ።

በዚሁ ረገድ በሁለቱ መንግሥታትና በሁለቱ ሕዝብ መካከል ያለው የሥልጣኔ ልዩነት ከፍ ያለ ነው ። ከክርስቶስ ልደት ቀደም ብሎ ካለው ጊዜ ጀምሮ እስከ መሐመድ ልደት ድረስ ሰባተኛ መቶ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ፖርቱጋልን በጥንታዊነት በነፃ መንግሥትነት በኃያልነትም በሥልጣኔም ትበልጣት ነበር ። ኢትዮጵያ በነዚህ ረጅም ዘመናት ራሷን የቻለች በሳባና በግዕዝ ፊደልና ቋንቋ እየጻፈች የምትናገር የሥነ ጽሑፍ ደረጃዋ ከፍ ብሎ የምትራቀቅ ፤ እንደ ሠለጠኑት እንደ ፋርስ እንደ ግሪክና እንደ ሮማውያን ነገሥታት በወርቅ በብር በነሐስ በነገሥታቷ መልክ በተሠሩ ገንዘቦች ስትገበያይ ፤ በደቡብ ዓረብ በመርዊ በኑብያ ድል አድርጋው ለተመለሱ ንጉሦቿ ክብርና መታሰቢያ በአክሱም እስከዛሬ ግማሾቹ ቆመው የቀሩት ወዳድቀው የሚታዩትን በከተማዋ በየአደባባዩዋ ረገርዥርምና ቅርፃቸው ያማረና ለተመልካች የሚያስደንቁ ሐውልቶች ስታቆም ፤ የጦርና የንግድ መርከቦቿ በቀይ ባሕር ላይ ሲንሳፈፉ የቍስጥንጥንያ ነገሥታት እነ ቄሣር ቆስጥንያኖስ የኢትዮጵያን ነገሥታት እነ አብርሃን (ዒዛና) እንደ ወንድም እንደ ጓደኛ በሚቆጥሩበት ሰዓት ፖርቱጋል ግን መጠሪያ ስሟ ሉዚታንያ እየተባለች እስከ አምስተኛው መቶ ዓ. ም. ድረስ ለሮማ የቄሣር መንግሥት እንደ የአውራጃ ግዛት ነበረች (1) ።

ሮማውያን ደከም ሲሉ አሌን ሱኤቨ ፤ ቪዚጎት የሚባሉ የጀርመን ዘሮች ከአምስተኛው መቶ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ስምንተኛው መቶ ዓመት ድረስ ተተክተው ሰሜን አፍሪካንና ኢስፓኝን የወረሩት ዓረቦች ከስምንተኛው እስከ አሥረኛው መቶ ዓ. ም. ድረስ በገዥነት ሲሻሙዋት ሲቀራመቷት ቆይተው ፖርቱጋል ያን በኛ ንጉሣዊ መንግሥቷን አቁማ በራሷ መተዳደር የጀመረችው እንደ ኢትዮጵያ ሥልጡኑ የአክሱም መንግሥት በዚሁ በዓረቦች እንግሥ ወድቆ የዛጉዬ መንግሥት በሚያስተዳድርበት በ፲፩ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ነው ።

ከዚህ ጊዜ ቀደም ብለው አስቴሪዎ የሚባሉት የክርስቲያን ወገኖች እስላም
ቹን ተዋግተው በመደምሰስ ሊስቦን ገብተው በዚህ በአሥራ አንደኛው መቶ ዓ.ም.
ላይ የፖርቱጋልን መንግሥት አቋቋሙ ። ከአሥራ ሁለተኛው እስከ አሥራ አራ
ተኛው መቶ ዓ. ም. በካስቲይና በፈረንሳይ አገር የተዘረጋው የቡርጎን ዘር በሔንሪ
ጀማሪነት ተተክሎ ሲገዛ ከኖረ በኋላ ሐቪዝ (አቪስ) ለተባለው ሥርወ መንግ
ሥት አሳለፈው ። በዚህ ሥርወ መንግሥት (ዲናስቲ) ዮሐንስ አንደኛውና ሁለተ
ኛው ፤ አማኑኤል ሀብታሙ የሚባሉት ታላላቅ ነገሥታት እየተነሡ በአጭር ጊዜ
ውስጥ ፖርቱጋልን ኃያልና ታላቅ መንግሥት አደረጉት (2) ።

ስለዚህ በአሁኑ በአሥራ አምስተኛውና በአሥራ ስድስተኛው መቶ ዓ.ም.
ላይ የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ገናንነትና ሥልጣኔ ሲመዘን የነገ
ሢጦሽ ሆኖ በሥልጣኔ ሥፍራ ለሥፍራ ተለዋውጠው ሥልጡኑ ወደኋላ ሄዶ የጥን
ትትን ሥፍራ ቢይዝ ሞኙ ከሞኝነት ኑሮው ተራምዶ የሥልጣኔን ደረጃ ይዞ ይገኛል ።

(1) የኢት. ታሪክ -- አክሱም -- ዛጕዬ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕ. 51 ገጽ 309 - 301

(2) Encyclopedia Britannica 18 Vol. ገጽ 273 - 297

ወንጌል የፊተኞች የኋለኞች ይሆናሉ እንዳለው ሥልጡኑ ገናናው ባለመርከቡ ባለሐውልቱ የአክሱም መንግሥት ወድቆ በዚህ በ፲፮ኛው ዘመን ያለችው ኢትዮጵያ ነፃነቷን መንግሥቷን ባታጣውም ያልሠለጠነችና ደካማ ሆና በርሷ እንጻር የተንቱ ደካማ የፖርቱጋል ሕዝብ የሠለጠነ የሰፋፊ አገር ገዥ የጦር መርከቡና የባሕር ኃይሉ በየወደቡ ቁርኮችን የሚያስፈራ ኃያል መንግሥት ሆኗል ።

ይህ የሥልጣኔና የገናናነት ልዩነት በምን ምክንያት ደረሰ ? ምንጩስ ምንድነው ? ብለን የተመራመርን እንደሆነ የዚህ ዘመን ኢትዮጵያ አክሱሞች ከብዙ ዘመን በፊት የጀመሩትን ሥጋዊ ሥልጣኔ ችላ ብላ ከዚህ በፊት እንደተባለው ያለው የአቅሟ ኃይል በመንፈሳዊና በሃይማኖት እንደዚሁም በቆየ ልማድና ወግ ተያዘ ። የርሷ ሊቃውንትና ፈላስፎች በራቀው ዘመን በብሉይ ውስጥ ያሉትን ሙሴ ኢያሱ ዳዊት ሰሎሞን ሲራክ ወይም የነዚህን መጻሕፍት አጠናቀው ያወቁት ሆኑ ። የሥልጣኔዋና የፍልስፍናዋ ምንጭ ብሉይና ሐዲስ የሊቃውንት መጻሕፍት ሆኑ ። እንደ ግሪክ እንደሮማ በሠለጠነ አገር ሳትገዛ መቅረቷ ለትምክህት ሲያገለግላት ባንድ ወገን ከገዥ የሚገኘው ሥልጣኔ እንዳመለጣት ግልጽ ነው ።

የፖርቱጋል ሕዝብ ግን ሥልጣኔን ከግሪክ ደኅና አድርጎ በቀዳው ራሱም ደኅና አድርጎ በሠለጠነው በሮማ መንግሥት ሥር ብዙ ዘመን ስለተዳደረ የሮማን ሥልጣኔ የነቪርጂልን ግጥም ፤ የነሴኔክን ፍልስፍና የነዩልዮስ ቄሣርን የጦር አመራርና ድርጅት የነሲሴሮን የአነጋገርና የፖለቲካ ስለ ISIC ጨብጠው ተነሡ ። የፊተኞቹም የግሪኮቹ የነሶክራት ፤ የነፕላቶን ፤ የነአሪስቶት ፤ የነሶሎን የኑሮና የአስተዳደር ፍልስፍና የነሂፖክራት የሕክምና ዕውቀት ፤ የነፔሪክል ፤ የነሌዎኒዳ ፤ የነአስክንድር የጦር አመራር ዘዴ አላመለጣቸውም ። ማናቸውንም ዕውቀት በየዘርፉ ከመቅሰም አላረፉም ። የዕውቀቱን መጽሐፍ ከግሪክ ወደላቲን ፤ ከላቲን ወደ ቋንቋቸው በመመለስና በመማር ተጠቅመዋል ።

የቤተ ክህነቱም ክፍል በላቲናዊው ሥልጣኔ ላይ የሃይማኖት መሠረት የሆነውን ብሉይና ሐዲስን ሳይለቅ ከቤተ መንግሥቱ ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ በመሥራት ለመንግሥቱ ድጋፍ ሆኖ በሥራ ስለተባበረ የመንግሥቱ ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄደ ።

በሮማ የመንግሥቱ አስተዳደር በደንብ ተዘጋጅቶ የታወጀ መተዳደሪያ ሕግ (DROIT ROMAN) የተመረጡ ያገርን ጉዳይ የሚወስኑ መማክርት (SENAT) ከግሪክ የተቀበሉት ራሳቸው አሻሽለው የሚጠቀሙበት የታሪክ የሥነ ጽሑፍ እርምጃ የቤት ሕንፃ ሥራ የደንገያ ቅርፅ የስዕል ሙያ የጦር መሣሪያ የነፍጡና የመድፉ የመርከቡ ሥራ በያይነቱ ሮማውያን የነበራቸውን የፖርቱጋል መንግሥት በዚህ ጊዜ ወርሶ በፋንታው ከማሻሻል ጋር ስለተጠቀመበት ከሮማውያን የወረሰው ሥልጣኔ በጠቅላላው በአሁኑ በ፳ኛው ዘመን ያለበትን የኃያልነት ደረጃ ሰጠው ማለት ነው ።

ፈረንጆች «የወርቅ ዘመን» የሚሉትን በኛ «የአዱኛ ዘመን» ብለን ልንተረጉመው የምንችለውን የፖርቱጋልን የገናናነቱን ዘመን ባለታሪኮች በ፲፬፻፲፭ -



የእስጢፋኖስና የክርስቶፎሮስ አባት ስመ ጥሩው መርከበኛ ቫስኮ ደጋማ

፲፭፻፹ ዓ.ም. መካከል መድበውታል ። በዚህ ዘመን በተለይ ከአሥራ አምስተኛው መቶ ዓ. ም. ወዲህ እንግሊዝም ጀርመንም ኤስፓኝና መስኮብም ቱርክም በየ ፊናቸው እንደ ኃያላንና እንደ ሰለጠኑ መንግሥታት መቆጠራቸው ባይቀር ከነ ዚህ ሁሉ የፖርቱጋል መንግሥት በሌላው እንኳ ቢቀር መርከብ በመሥራት በመ ርከብ አገር ላገር እየዞሩ ወርቅና ሀብት ያለበትን እየመረመሩ ብዙ አገር በመያዝ ከቀሩት አገሮች ይበልጥ ነበር ።

የቀሩት የአውሮፓ ነገሥታት በመጀመሪያው ጊዜ ላይ እዚያው ከወሰናቸው ላይ በሚገኘው መሬትና በሚያዋስኑዋቸው ታናናሽ መንግሥታት ላይ ገዥነታቸ ውን ለማጽደቅ እርስ በርሳቸው ሲጣሉ ሃይማኖትን ለማሻሻል ወይም ላለማሻሻል ሲጨቃጨቁ የፖርቱጋል መንግሥት ግን ካራቬላ የሚባለው ክብደቱ ዝቅተኛ ቢሆንም ለዘመኑ ፈጣን የሆኑ መርከቦች በባሩድ የሚተኮሱ ነፍጦችና መድፎች እየሠራ ወታደር እየመለመለ መጀመሪያ በአቅራቢያ የሚገኘውን የሴውታን ከተማ (ማሮክ) በ፲፬፻፲፰ ዓ. ም. ከያዘ በኋላ ቀጥሎ ከመንግሥቱና ከአውሮፓ ርቆ የሚገኘውን የአፍሪካን የደቡብ አሜሪካን ፣ የእስያን አገሮች ያስመረምር ጀመር (1) ።

ለዚህ ምርመራና አገር መያዝ በፖርቱጋል በዚህ ዘመን ባለው የምርመራዋና የአገር ማቅናቷ ታሪክ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዘው የሚገኙት ከፖርቱጋል ተነሥቶ ታቹን በቦን ኤስፔራንስ ደቡብ አፍሪካ በኩል ዞሮ ፲፬፻፹ ውቅያኖስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያቋረጠው ቫስኮ ደጋማ ፤ የቤተ መንግሥቱ ተወላጅ መርከበኛው ሐንሪ ፣ ከዚ ያም እነፔሬዝ ፤ እነ እንድራዴ ፣ እነ ካብራል ፣ እነዳልሜይዳ ናቸው ።

እንደ አው. ቍ. ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፭፻ ዓ. ም. አልቫሬጽ ካብራል የተባለው የጦር መኰንን በትልቅ መርከብ ሄዶ የብራዚልን አገር አስገበረና በፖርቱጋል መንግሥት ስም ቀኝ አገር አደረገው ። ከዚያም በተገኘው ወርቅ መንግሥቱ ከበረ። ፍራንቼስኮ ዳልሜይዳ ቫስኮ ዳጋማ ደርሶ መርምሮ ከተመለሰ ወዲህ ወደ ሕንድ በመርከብ ዘምቶ አገሩን ከያዘ በኋላ የመጀመሪያው የንጉሥ እንደራሴ ተብሎ ያስ ተዳድር ጀመር ። ሁለተኛው እንደራሴ አልፎንስ አልቡኬርክ የፖርቱጋልን ገዥ ነት በሕንድ ያስፋፋና በ፲፭፻፲ ዓ. ም. ጎአን የያዘ ነው ።

በዚህ የጦር መኰንን ዘመን ነው የፖርቱጋል መርከበኞች እስከ ቻይና ድረስ ዘልቀው እስከ ዛሬ ድረስ በእጃቸው ያለውን የማካዎን በማሌዚያ የማላካን ከዚያ ኒውጊኔን ቲሞርን መያዝ የቻሉት ።

ከወዲህም የአፍሪካን የወደብ ግዛታቸውን ከሕንድ የወደብ ከተማቸው ጋር የሚያገናኘውን በፋርስ ባሕር ውስጥ የሚገኘውን ሆርሙዝ የሚባለውን ደሴት በ፲፭፻፲፭ ዓ. ም. ያዙ ። በዚህ ምክንያት ከነዚህ ሰፋፊ ግዛታቸው በአውሮፓ የማ ይገኘውን የምሥራቅ ሸቀጣ ሸቀጥ ቅመማቅመም ለአውሮፓ የአውሮፓን ዕቃ ለነዚያ በመርከብ እያመላለሱ መንግሥታቸውን በንግድ አከበሩት ። በዚሁ የተነሣ

(1) Histoire generale de l'Afrique- Presse-Universitaire...... ምዕ. 111 ገጽ 213 - 216




ፍራንቸስኮ ዳልሜይዳ (ከካሜራር - መጽሐፍ ላይ የተገኘ)

ንጉሣቸው አማኑኤል (፲፬፻፺፭ - ፲፭፻፳፩) ሀብታሙ ንጉሥ በሚል ቅጽል ስም ይጠራ ጀመር (1) ።

ፖርቱጋል በዚያው በአገሩ ውስጥ ሌሎች የአውሮፓ አገሮች የሚጠቀሙበት የዕውቀት ፤ ያገር ካርታ ፤ የሒሣብ በተለይ የከዋክብት የቅርጽ ፤ የሥዕል ፤ የሕንፃ ሥራ የሥነ ጥበብና የሥነ ጽሑፍ እርምጃ ከማድረግ አልቦዘነም ። ለቅዱሳኖቻቸው ያሠሩት የቤተ ክርስቲያንና የገዳማት ሕንፃዎች ከነሥዕሎቻቸው እስከ ዛሬ እገር ጐብኝን ያስደንቃሉ ። የመጀመሪያውን ዩኒቨርሲቲ በኮይምብራ በ፲፭፻፴፯ ዓ.ም. ያቆመ ዓፄ ልብነ ድንግል ደብዳቤ የጻፉለት ዮሐንስ ሣልሳዊ የሚባለው ንጉሥ ነው ።

ኢትዮጵያ ግን በዚህ ጊዜ ከሥልጣኔ ርቃ በአገሯ ክልል ውስጥ ድምጿን አጥፍታ ከመቀመጥ በቀር ከግሪክና ከሮማ የመነጨውን የአውሮፓን ሥልጣኔ በየመልኩ ሳትሳተፍ ስለቀረች እነዚያ ከጠላት የሚከላከሉበት ወይም ጠላትን የሚያጠቁበት በባሩድ ኃይል ራቅ ብሎ ሄዶ የሚመታ የመድፍና የጠበንጃ መሣሪያ ከነጥይቱ ሲሠሩ እርሷ አብዛኛጊዜ ለጨበጣ ጦርነት ከሚያገለግለው ከነዋሪው የጦርና የጐራዴ መሣሪያ አልወጣችም ። ከነዚህም ጋር ጭማሪ ቢኖር ቀስት ዱላና ኘራፍ እንካሴና እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው ። ከጥጥ ከሚሠራው ሸማ በቀር የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖች የሚጠቀሙት በጥበብ የተሠራውን የሐር ልብስ ፤ ካባውን ፤ ቀሚሱን ጥላውን ሥጋጃውን ከዓረብ ከሕንድና ከፋርስ በወርቅ እየገዙ ነው ። እነዚያ በሚያማምር የድንጊያ የሕንፃ ቤታቸውን እየሠሩ ሲቀመጡ ከድንጊያ አልፈው ነገሥታቱ መሳፍንቱ ቤታቸው በዕብነ በረድ ሲሠራ የኛዎቹ በዚህ ጊዜ ከእንጨትና ከጭቃ ቤት ቢበዛም ከማያምር የድንጊያ ሕንፃ ወይም ካብ ቤት አልተላቀቁም ። ስመ ጥሩው ንጉሠ ነገሥት ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥታቸውን ያሠሩት ከየአውራጃው በትዕዛዝ በተሰበሰበ ወፍራም እንጨትና በተላጠ አጠና መሆኑን የራሳቸው የግዕዙ ዜና መዋዕል አብራርቶ ይገልጻል ። በሚያምር ሕንፃ የመሠራት ዕድል ቢያጋጥመው ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ነው (2) ።

ISIC

የአውሮፓ ሸቀጥ ወደ ኢትዮጵያ ስለአልገባ ከኢትዮጵያም በኢትዮጵያዊ እጅ የተሠራ ተብሎ ወደ ፈረንጅ አገር ማናቸውም ዓይነት የእጅ ሥራና ሸቀጥ ስለ አልወጣ አገሪቱ ራሷ ለአውሮፖች የተሠወረች አገር ሆነች ። በአውሮፓና በውጭ አገር ካለመታወቋ የተነሣ የኑሮዋን ጭምጭምታ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ከኢትዮጵያውያኑ ምእመናን ጋር ተገናኝተው የተመለሱ ያወሩ ጀመር ። ሲወራም ቄሱ ዮሐንስ በሚባል ንጉሥ የምትተዳደር አንድ የክርስቲያን አገር አለች ፡ ሥፍራዋ በምሥራቅ በሕንድ ይሁን ወይም በአፍሪካ አይታወቅም የሚሉ ወሬ ደጋግሞ ስለተሰማ የፖርቱጋል ጦር በአፍሪካ ሰሜን በማሮክ በታንገር በአልገሬ ታቹ

(1) Le routier de Dom Joao De Castro A. Kammerer ገጽ 1 - 4 ።

(2) የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 33

ንም ወደ መካከል ወደ ኮንጎ የገባ ጊዜ ዳግማዊ ዮሐንስ (፲፬፻፹፩ - ፲፬፻፺፭) የሚባ ለው የፖርቱጋል ንጉሥ ፔድሮ ደ ኮቪሊሐእንና አልፎንሶ ዶፓይቫን "ሂዱችሁ ይቺን አገር ተፈላልጋችሁ አግኙ" ብሎ እስከ መላክ ደረሰ (1) ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የፖርቱጋል የጦር መርከብ በቀይ ባሕር እየተመላለሰ በተ ለይ በ፲፭፻፲፩ ዓ. ም. የግብፅን መርከቦች ካጠፋ ወዲህ የፖርቱጋል መንግሥት ታላ ቅነትና ክርስቲያን መሆኑ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ በሚገኙት የውጭ አገር ሰዎች በራሱም በደኮቪልሐእ አንደበት እየተነገረ ዝናው በኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ እየተስፋፋ ይሰማ ጀመር ።

ይልቁንም እላይ ስሙን የጠቀስነው ፔድሮ ዶኮቪልሐእ ባኤ እስክንድር ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ ወዲህ የፖርቱጋል መንግሥት በኢትዮጵያ በጣም የታወቀና ተስፋ የሚደረግበት ሆነ ። በዚህ ዘመን ለመንግሥት እንደራሴ ወይም ሞግዚት የነበሩት ያኤ በዕደ ማርያም ባለቤት ንግሥት እሌኒና ዓፄ ልብነ ድንግል የዝምድና ደብዳቤ ከፖርቱጋሉ ንጉሥ ከአማኑኤል ፤ በኋላም ከተከታዩ ከዮሐንስ ጋር መጻጻፍ የጀመሩት በዚህ ምክንያት ነው ። ከተጻጻፉም በኋላ በግራኝ ወረራ መጨረሻ ጊዜ መጥተው ኢትዮጵያን የረዱት ፖርቱጋሎች በዚሁ መሠረት ነው ። ርዳታውም ባንድ ወገን የክርስቲያንነት ዝምድና ቢኖርበትም በሌላው ወገን የግ ዛት መስፋፋትም አሳብ እንደነበረበት የታወቀ ነው ።

ነገር ግን የዓፄ ልብነ ድንግል የክርስቲያንን መንግሥት ድጋፍ ከውጭ አገር ሲያገኝ ተቀናቃኝ የሆኑት ፤ የሐረርና የአዳል እስላሞች ደግሞ በበኩላቸው የእስ ላም መንግሥት የሚሆን ድጋፍ ካገኙ ብዙ ጊዜያቸው ነው ። እነዚህም መጀመሪያ የዓረብና የግብፅ መንግሥታት ናቸው ። እንደ አውሮፓ ቍጥር በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ቱርክ ግብፅን ካስገበረ በኋላ ቱርክም የበላይ ረዳት ሆናቸው ።

እንዲያውም ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሩቅ አገር ከአውሮፓ ምዕ ራብ ወይም ከማዛቱ ከሕንድ ርዳታ ሲጠብቅ የአዳሎችና የሱማሌዎቹ መሪዎች ግን ከዋናው ከቱርክ መንግሥትና ይልቁንም የርሱ ጥገኛና ተገዥ ከሆኑት ኢትዮ ጵያን ከሚያዋስኑት ከግብፅ ከየመንና ከዘቢድ ጋሻዎች በቅርብ ርዳታ በማግኘ ታቸው እያደር አይለው በመጨረሻም በግራኝ አህመድ መሪነት መላ ኢትዮጵያን ለመውረር መቻላቸውን ወደፊት በዝርዝር ልንመለከት ነው ።

በመጨረሻም የቱርክ መንግሥት የአውሮፓን ምሥራቅ ፤ የአፍሪካን ሰሜን ይዞ ካስገበረ በኋላ ወደ የመንም ፤ ወደ ኑብያም ገብቶ ሲመሠረት የኢትዮጵያ ጠረ ፍ ወደ ሆነው ወደ ሱዋኪንም ደርሶ ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ምጥዋን ያዘ ። ፖርቱ ጋሎቹም ሕንድን ከያዙ ወዲህ በኢትዮጵያ ዙሪያ በቀይ ባሕር ዳርና ዳር ከቱርክ ወታደር እየተሻሙ አገር የሚይዙበት ከኢትዮጵያም ጋር እነኮቪልሐእን እየላኩ የዝምድናና የፖለቲካ ወዳጅነት የመጠኑበት ጊዜ ስለሆነ ይህ የወዳጅነት ውጥን

(1) የኢት. ታሪክ ካኤ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ገጽ. ፵፬ ፤ La Mer Rouge l'Abyssinie - A. Kammerer Tome 2ᵉ ገጽ 10 - 17

መጀመሪያው ጊዜ ኢትዮጵያን ሊጐዳ ችሏል ። ሊጐዳም የቻለው የፖርቱጋል ርቀትና የነዚህ የዓረብ አገሮች ቅርበት ነው ።

ስለዚህ ቱርክ ወይም በቱርክ ጥገኝነት ውስጥ ያሉት ግብፆችና ዓረቦች በኢትዮጵያ ያሉትን እስላሞች በመደገፍ ክርስቲያኑን መንግሥት ለመገልበጥ ሲመኙ የፖርቱጋል ወታደሮች ደግሞ በሩቅ ዝናውን ሲሰሙት የኖሩትን የኢትዮጵያን መንግሥት አግኝተው የዚህን መንግሥት መሣሪያነት ካገኙ በኋላ ግዛታቸውን በአፍሪካ ዙሪያ ለማስፋፋት ምኞት ነበራቸው ። ነገር ግን እላይ እንዳልነው የነርሱ የናት አገር ፖርቱጋል የቅኝ ግዛታቸውም ከመራቁ የተነሣ ስለአፍሪካም ግዛት ያላቸው ምኞት አንድ አንድ ጊዜ በመቀዝቀዙ ከሁለቱም ወገን በተወጠነው ወዳጅነት ምክንያት ክርስቲያናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ለጊዜው ብቻውን በግራኝ ወረራ ፊት ተሠዋ ። ይሁን እንጂ መጀመሪያ ብቻውን ፲፬ ዓመታት ያህል ከተሠዋ በኋላ መልሶ ሕይወት ያገኘው በነርሱ ርዳታ መሆኑ አይጠረጠርም ። ይኸንንም ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፲፩

## የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ግንኙነት - ንግሥት እሌኒ በማቴዎስ እጅ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ወደ አማኑኤል የላኩት ደብዳቤ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት መደቡ ካላስታ ወደ ሸዋ ከዞረ ወዲህ ነገሥታቱ እነ ዓምደ ጽዮን እነዓፄ ይስሐቅ ፤ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የቀሩትም ሁሉ በየጊዜው ከአዳልና ከይፋት የእስላም ባላባቶች ጋር ብዙ ጊዜ ያደረጉትን የማሳመን ጦርነት በ፪ኛው ቮሊም ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚለው መጽሐፍ አመልክተናል ።

ይኸንንም ጦርነት ለማስቀረት ነገሥታቱ እነበዕደ ማርያም እነናዖድ ከደዋሮው ከአዳሉ ባላባቶች ጋር ቢጋቡም የፖለቲካው ጋብቻ የጦርነቱን በር ሊዘጋው አልቻለም ። ደዋሮው ሲገዛ አዳሉ እምቢ ባይ ነው ። አዳሉ ሲሸነፍ ሱማሌው ይነሣል ። ስለዚህ የመንግሥቱ ዋና ሞግዚት ንግሥት እሌኒ ለአዳሎችና ለሱማሌዎች መሣሪያ እየሰጡ ጉልበት የሆኑዋቸው የግብፅና የዓረብ አገሮች መሆናቸውን ስለሚያውቁት ወደነዚሁ አገሮች የወዳጅነት ደብዳቤ እየተላላኩ በየጊዜው የሚሆነውን ግጭት አቅልለውት ነበር ። ዳሩ ግን በዚህ ዘመን አጭር ታሪኩንና ፍጻሜውን ወደፊት የምንመለከተው ይማም ማኅፉዝ የዘይላ ሹም እስከላይ እስከ ፈጠጋር (ምንጃርና ቡልጋ) እስከ ደዋሮ (ከረዩና ጨርጨር) እስከ ይፋት ድረስ እየመጣ አገር እየዘረፈ በየጊዜው ስላስቸገረ የእርሱ ደጋፊና የሃይማኖት አንድነት ካላቸው አገሮች ከግብፅና ከዓረብ አገሮች ጋር በደብዳቤ መዛመድ መሠረት እንደማይሆን ተረዱት ።

በዚህ ምክንያት የነዚያን ወገን ችላ ብለው ከሁሉ ይልቅ ከክርስቲያኑ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር መዛመድ የሚሻል መሆኑን ገምተው አሳባቸውን ወሰኑ ። የፖ

ISIC

ርቱጋል መንግሥት ባንድ ወገን የቱርኮችና የዓረቦች የሃይማኖትም የግዛትም ባላንጣ በመሆኑ ፡ ምንም እንኳን ለክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አለው የሚል ካቶሊካዊ ቢሆን በጠቅላላው ክርስቲያን በመሆኑ የሁለቱም ዓይነት ሁኔታው ከኢትዮጵያ ጋር ሊያዛምደው ምክንያትና መንገድ መስጠቱ የታወቀ ነው ። ባለፈው ደግሞ እንዳመለከትነው በዓፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት መጥቶ በቤተ መንግሥቱ ባለሟል ሆኖ በክብር የተቀመጠው ፔድሮ ዴ ኮቪልሐኦ (PEDRO DE COVILHAO) በሕንድ የፖርቱጋሉ ንጉሥ እንደራሴ በዚሁ ዓመት የላካቸው ሁለት መልክተኞች የዚህኑ የግንኙነት መንገድ የፖርቱጋልን መንግሥት ታላቅነቱንም ክርስቲያንነቱንም ከዓረቦች ጋር ያለውን ጠብ እያስረዱ መንገዱን ደኅና አድርገው ሳይደለድሉት አልቀረም (1) ። የነርሱንም አሳብ የሚደግፉ ከቍስጥንጥንያ ከኢየሩሳሌም ከሶርያ ከአርመንያ የመጡ የውጭ አገር ተወላጆች የሃይማኖትም የመንግሥትም ሥራ ለቤተ መንግሥቱ ለግላቸውም የሚሠሩት ምንም እንኳን ፖርቱጋል ካቶሊክ መሆኑን ቢያውቁ ለጊዜው በፖለቲካው ምክንያት ከዚህ መንግሥት ጋር ከመዛመድ በቀር ሌላ የመውጫ መንገድ እንደሌለ ሳይመክሩ አልቀሩም ።

ስለዚህ ንግሥት እሌኒ ከእስላሞቹ ጋር የጀመሩትን የወዳጅነት ግንኙነት ሳያቋርጡ በምሥጢር ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ለመወዳጀት ገጸ በረከትና ደብዳቤ ማዘጋጀት ጀመሩ ። ይኸውም ፲፭፻ የሚያስረዳን መልክተኛው ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ሄዶ ሳይመለስ በመካከሉ እንደ አውሮፓ አቈጣጠር በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. (እንደ እስላሞች የሒጅራ ቍጥር ፱፻፳፪) ላይ ገጸ በረከትና ደብዳቤ ለግብጹ ንጉሥ ለማመስከ ከንሱህ ኤል ጉሪ (QANSOUH EL GOURI) መላካቸው ነው (2) ።
(QANSOUH EL GOURI የሚባለውን ደኸን የግብፅ ሱልጣን አንዳንድ ጸሐፍ ኤል ጋውሪ ይሉዋል ። እርሱም የነገሠበት ዘመን እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፩ - ፲፭፻፲፮ ዓ. ም. ነው (3) ።

የሆነ ሆኖ እቴጌ እሌኒ ያዘጋጁትን ደብዳቤና ገጸ በረከት ፔድሮ ደ ኮቪልሐኦ እንዳይወስድ ባጠገባቸው እንደማያገኙም ባይሆን ብዙ ሐሳብና ምክር እየሰጠ የሚያጽናና ስለሆነ እርሱን ትተው ለመልእክቱ ማቴዎስ የሚባል የአርመን ተወላጅ መረጡ ። እርሱም የተመረጠበት ምክንያት ክርስቲያንና የቤተ መንግሥቱ ታማኝ ከመሆኑም በላይ በንግድ ምክንያት ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ግብፅ ወደ ሕንድ እየተመላለሰ አገርና ቋንቋ በማወቁ ሳይሆን አይቀርም ። ሁለተኛም አገሩ አርመን በቱርክ ግዛት ውስጥ ስለሆነ ውስጡን የኢትዮጵያ ወዳጅ ሆኖ ላዩን የቱርክ መንግሥት ዜግነት አያጣምና በየበሩ ፡ በጠረፉ የእስላሞቹ ባለሥልጣኖች ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የሚመላለሰውን በማሠር በመፈተሽ የሚያደርሱትን ችግር በርሱ ላይ አይፈጽሙበትም ተብሎ የታሰበ ይመስላል ። እነሆዱም እንደነጋዴ መስሎ ስሙንም

(1) የነዚህ መልክተኞች ስም በማቴዎስ እጅ በተላከው ደብዳቤ ውስጥ የሐንጋሪ ... ተብሏል
(2) ባሴት ሬኔ የኢት. ታሪክ ጥናት ማስታወሻ ፲፱ ። ገጽ 141 - 142
(3) ኢትዮጵያውያን በፓለስቲን የሚባለው የቸሩሊ መጽሐፍ አንደኛ ክፍል ገጽ ፫፻



አልፎንሶ ደ አልቡኬርክ (ከካሜሬር መጽሐፍ ላይ የተገኘ)

ኢብራሂም (አብርሃም) አስገኝቶ እንጂ እንደ መንግሥት መልክተኛ ሆኖ አይደለም (1) ።

ስለዚህ ማቴዎስ እንደ አውሮፓ ቍጥር በ፲፭፻፲ ላይ (እንደ ኢት. ቍጥር ክርስቶስ ፲፭፻፱) ዓ. ም. ከንግሥት እሌኒ ደብዳቤውን ይዞ ለጉዞ ተዘጋጀ ። ከርሱም ጋር አብሮ የሄደ ፩ ኢትዮጵያዊ ነበረ ። ነገር ግን በመንገድ ሞቶ ይባላል ። ማቴዎስ ግን ገጸ በረከቱን ይዞ ወደ ሕንድ ተጓዘ ። ወደ ሕንድ መሄዱ ወደ ሊስቦን የሚመላለስ መርከብ ያን ጊዜ ማዛታቸው ከነበረው ከሕንድ እንጂ ከሌላ ዘንድ እንደ ልብ ስለማይገኝ ነው ። ማቴዎስ ሕንድ ግዛት በተለይ ዳቡል እሚባለው ከተማ ደረሰ ። በዚያም የፖርቱጋሉን አገረ ገዥ አግኝቶ ወደ ሊስቦን ከኢትዮጵያ መንግሥት ተልኮ የሚሄድ መሆኑን ገልጾ ማናቸውንም ርዳታ እንዲያደርግለት ጠየቀው ፡ አገረ ገዥው የተላከህበትን ጉዳይ ግለጽልኝ ቢለው አልችልም አለው ። አገረ ገዥው በዚሁ ማቴዎስን ተቀይሞ የቱርኮች ሰላይ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አሰረው ፡ የዚህን ወሬ በሕንድ ዋና ከተማ በጐአ የሚቀመጠው ከዚህ በፊት መልክተኞች የላከው ዋናው የንጉሡ እንደራሴ አልቡኬርክ ( Albuquerque ) ሰምቶ አስፈትቶ ወደጐአ ወሰደው ። እርሱም እንደዚያው እንዳገረ ገዥው መልክተኛው የያዘውን ጉዳይ ለማወቅ ፈልጎ ማናቸውንም የሚያስፈልገው ርዳታ ሠምሮ ወደሊስቦን እልክሀለሁና ለኔ ንገረኝ ቢለው ማቴዎስ የተላክሁት ከፍ ያለ ምሥጢር ነገር ስለሆነ ለራሱ ለንጉሡ ካልሆነ በቀር ለማንም አልነግርም ብሎ እምቢታውን ስላጸና የንጉሡ እንደራሴ ስሞኑን ሁሉ ፈትቶ ነስቶት ሰነበተ ይባላል (2) ። ይሁን እንጂ በመጨረሻ እንደራሴውም በዚያ ያሉት የፖርቱጋል መኳንንትና ቀሳውስት የኢትዮጵያን ክርስቲያንነት ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ሊኖር የታሰበውን የወዳጅነት ግንኙነት በመረዳት በመጨረሻ መልክተኛውን በክብር ያዘው እስተ ናግደው ራሳቸው በመርከብ አሳፍረው ወደ ፖርቱጋል ሰደዱት ። ማቴዎስም ማናቸውንም የጉዞ ችግር ታግሦ ኢትዮጵያን በለቀቀ በሦኛው እንደሌሎቹ በ፬ኛው ዓመት እንደ ኤው. ቍጥር በ፲፭፻፲፬ ዓ. ም. እዋናው ከተማ ሊስቦን ደረሰና ከንግሥት እሌኒ የተላከውን ደብዳቤና ገጸ በረከት ታላቁና ዕድለኛ ለሚባለው ለንጉሡ ለአማኑኤል አስረከበ ።


የደብዳቤው የግዕዙ ትክክለኛ ቅጅ ከፖርቱጋል በለጠፋ አይገኝም (3) ። ይህ ደብዳቤ በዚያው ዘመን ወደ ፖርቱጋል ተተርጉሞ ቀጥሎ ከፖርቱጋል ወደላቲን፣ ከላቲን ወደ ቶስካን (ኢጣልያ) ከቶስካን ወደ ቀድሞ ፈረንሳዊኛ ተተርጉሞ ትክክለኛው ጽሑፍ ግን ቴምፖራል የሚባል ባሳተመው ላይ ስለሚገኝ ከዚያ ላይ እነሆ እንደተቻለ ወደ አማርኛ ተርጉሜዋለሁ ።

(1) የአፍሪካ ፪ኛ ቮሊዩም የመጨረሻው ክፍል ዠ ቴምፖራል ገጽ ፪፻፵

(2) የኢት. ታሪክ ጥናት ባሴት ሬኔ ማስታወሻ ቍ. ፻፲፱ ።

(3) አ. ካሜረር ቀይ ባሕር በሚል እርእስት የጻፈው ገጽ ፶፪ ። ከዚያ የሌቶ የተገኘው በአከተር ሥርግው እማካይነት ሮማ ላይ ባለፈው ዓመት ለተደረገው ለኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ የቀረበው የግዕዙ ደብዳቤ አቅራቢው እንደተገነዘቡት በውስጡ ስሕተት ስለአለበት ለመቀበል አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል ። በጠቅላላው ግን ከፈረንሳዊው ትርጉም ጋር ይመሳሰላል ።

ISIC



ንጉሡ አማኑኤል በቤተ ክርስቲያን ሲጸልዩ ።

እሊኢ ንግሥት ለአማኑኤል የጻፉት ይህ ደብዳቤ እንደዘመኑ በግዕዝ ቋንቋ መሆኑ አይጠረጠርም ። አማርኛ የሕዝብ ቋንቋ መሆኑ ሳይቀር በዚያን ዘመን ከዚያም ወዲህ በጕንደር የነበሩት ነገሥታት ደብዳቤ የሚጽፉት በግዕዝ ነበር ። ነገር ግን ይህ ግዕዝኛ ደብዳቤ ባለፈው እንደተመለከትነው በፈረንጅ የግዕዝኛ እውቀት ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ሲተረጐም ከአሳብ እንኳን ባይሆን ከንግግር ቅርጽ መዛነፍ የማይቀር ነው ። የሆነ ሆኖ ከቀድሞው ፈረንሳዊኛ እኔ እንደዚህ ብዬ ተርጕሜዋለሁ ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ወሠለስቱ አካላት ። በቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም የተወለደው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደኅንነት ጸጋና በረከት በጣም ለተወደደው በጣም ክርስቲያን ለሆነው ወንድማችን ለአማኑኤል የፖርቱጋል ንጉሥ ፥ የባሕር ገዥ ፥ ያረመኔዎችና የጨካኞች አሸናፊ ፥ እግዚአብሔር ጌታችን መልካም ዕድሉንና አሸናፊነቱንም በጠላቶችህ ላይ ይስጥህ ። የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ባበሠሩት በአራቱ ወንጌላውያን በቅዱስ ማቴዎስ ፥ በቅዱስ ማርቆስ ፥ በቅዱስ ሉቃስ ፥ በቅዱስ ዮሐንስ ጸሎት መንግሥትህም በየአለበት ያለው ግዛትህም ይስፋ ይረዝም ። ከትልቁ የጦር አለቃህ ከትሪስታን ዳ ኩኛ ዘንድ አንዱ ዮሐንስ (ጆሮ) ቶስ ነኝ የሚል ፥ አንዱም እንደሱ የመሰለ ዮሐንስ የሚባል ንጉሥ ተብሎ የተጠየቀ ሁለት መልእክተኞች ወደኛ መጥተው ስንት የጦር ወታደር መጠየቃቸውን እናስታውቅሀለን ። ከዚህም የተነሣ ወደ ኢየሩሳሌም ቁስ ስንልክ በሚባርከን በፓትሪያርክ ማርቆስ ፈቃድ በአገልግሎት ወንድማችን የሆነውን መልእክተኛችንን ማቴዎስ የሚባለውን ወዳንተ ላክነው ። ፓትሪያርክ ማርቆስም የኛና ያገራችን ሁሉ መንፈሳዊ አባት የቅድስት ሥላሴና የኢየሱስ ክርስቶስ የሃይማኖት ዓምድ ናቸው ። እስከ ሚያስፈልገው ድረስ ስንቅም ወታደርም ለመላክ የተዘጋጀን መሆናችንን በሕንድ ስለአዳኛችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለሚዋጋው የጦር አለቃህ እንዲነገረው መልእክተኛችንን ማቴዎስን አዘነዋል ። ምክንያቱም የክፉው መስፍን (ሱልዳን) ብዙ ወታደር ሰብስቦ ወታደሮችህን ሊወጋ አስቧል ማለትን ስለሰማን ነው ። ይኸም እንደሰማ ነው በሕንድ ያሉት የጦር አለቆችህ ያደረጉበትን ለመበቀል እንጂ ለሌላ አይደለም (1)።

በመጨረሻ በርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) የማያምኑት ወያቶንበሩ እንዲገቡ እግዚአብሔር በቅድስናው እነዚህን የጦር አለቆችህን በበለጠና በተሻለ እየጠበቀ ዘወትር ያበርታቸው ፥ በእነዚህም አረመኔዎች ላይ ብዙ ወታደር ልከን በባሕር ጠረፍ በመካ በሂጃ በባብኤል መንደል (ባብ ኤል መንደብ) ላይ ወያዥ ወደዚ ዳም (ጅዳ) ወደብ ወይም ወደቶር እንዲጠባበቁ ለማድረግ ችለናል ። ምክንያቱም ወደ ቅዱስ መቃብር (ኢየሩሳሌም) የምንልከው ስለትና ገጸ በረከት በነዚህ ................ እንዳይዋጥ .......... ።

አሁን ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ቅድስት ማርያም በፈረንጅ

(1) ሱልዳን ያለው ሱልጣን ማለቱ ይመስላል ።

አገር አንድ ንጉሥ ተወልዶ ....አረመኔዎችን ከዓለም ፊት ያጠፋቸዋል ብለው ትንቢት ተናግረው የነበረው የተስፋ ጊዜ እነሆ እንደደረሰ በውነት እንመለከታለን ።

መላክተኛችን ማቴዎስ የሚነግርህን ሁሉ እኛው ራሳችን እንደነገርንህ ቆጥረህ እመነው ። በቤተ መንግሥታችን ካሉት ከታላላቆቹ ሰዎች አንዱ እርሱ ስለሆነ ወደ አንተ ለመላክ መረጥነው ። ከዚህ በፊት የመጡት መልክተኞቻችሁ ጉዳያችንን የምንፈልገውን ያህል አልገለጹልህም ብለን ጠርጥረናል ።

በኢየሩሳሌም አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ከተሰቀለበት መስቀል (ግማደ መስቀል) ላይ የተሠራውን አንድ መስቀል በመላክተኛችን እጅ ልከንልሀል ፡ ከመጣልን ግማደ መስቀል ሁለት መስቀል አሠርተን አንዱን ለኛ አስቀርተን አንደኛውን በብር አንባር አሥረን ለአንተ እንዲያቀርብ ለመላክተኛችን ሰጥተነዋል ።

ከዚህም በቀር ደስ የሚያሰኝህ ቢሆን ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻችን ፡ ወንዶች ልጆቻችሁን ለሴት ልጆቻችን ሰጥታችሁን በሕግ ቢጋቡ ለኛ ደስ የሚያሰኘንና ለሁለታችንም የወንድማማችነት ዝምድና የሚመሠርት ትልቅ ጥቅም ነው ። ለዛሬውም ለወደፊቱም በጋብቻ ከናንተ ጋራ መዛመድን እንወዳለን፡

በተረፈ የአዳኛችንና የቤዛችን የኢየሱስ ክርስቶስ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ደኅንነትና ጸጋ ባንተና በልጆ[illegible]በቤተ ሰቦችህ ሁሉ ላይ ይውረድ ።

ከዚህ በላይ ከተነገረው በቀር የኛን የጦር ወታደራችንና ኃይላችንን ከናንተ ኃይል ጋር ብናደባልቀው እግዚአብሔር የተጨመረበት እንደሆነ የቅድስት ሃይማኖታችን ጠላት የሆኑትን ...... ለማጥፋት በቂ መሆኑን እናስታውቅሃለን ። አገራችንና ግዛታችን የሚገኘው ከባሕር ርቆ በየብስ (መሬት) ላይ ስለሆነና ምንም ወደብ ስለሌለን የባሕር ጦር ለማደራጀት አልቻልንም ። መርከበኛ ወታደርም የለንም ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና በሌላውና እንደዚሁም በባሕር ላይ የጦር ኃይል ካለህ ካንተ ጋር መደባለቅና ቃል ኪዳን ማድረግ አስፈለገን ። ባለፈው እንደነበረ አሁንም ለወደፊቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ረዳትህ ይሁን ። በሕንድ የሠራኸው ታላቅ ሥራ ጦርነትና ድል ተአምራት ነው እንጂ የሰው ልጅ ሊሠራው አይችልም ። ለሺ መርከብ የሚበቃ ስንቅና ማናቸውንም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በብዙ ልንሰጥ እንችላለን» (1) ።

እነሆ የደብዳቤው ቃል ይኸስ ይብዛ ይህ ነው ። ጉዳዩ ወደፍጻሜ ከመድረሱ በፊት በጕረቤቶች እስላሞች ዘንድ አደጋ እንዳያመጣ ይኸን ቃል ንግሥት እሌኒ ሲልኩ በጠበቀ ምሥጢር ማቴዎስን አደራ ብለው ነው ። መላክተኛውም ባለፈው እንደተመለከትነው በሕንድ ያሉት የፖርቱጋል ባለሥልጣኖች እንኳን የተላከህበትን ጉዳዩን ግለጽልን እያሉ በማሰርም በማባበልም ቢጐተጕቱት ምሥጢሩን

(1) Derniére partie du second tome de L'Afrique - Jean temporal 1556. ገጽ 130 - 133 ።

ሳያወጣ የንግሥቲቱን አደራና እምነት ሳያጐድል በትክክል ለንጉሡ ለአማኑኤል ብቻ በመስጠቱ የሚያስመሰግነው ነው ።

ግጸ በረከት ተብሎ የተላከው በኢትዮጵያ ታሪክ ከንጉ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በምዕራፍ ፳ ባዒ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ላይ እንደተመለከት ነው ከኢየሩሳሌም ከመጣው ግማደ መስቀል ላይ ተቆርጦ እንደመስቀል ተቀርጾ የተሠራ ነው ማለት ነው ። ይኸም ግማደ መስቀል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት እቴጌ እሌኒ የትልቁ ቆስጠንጢኖስ እናት ከተደበቀበት አግኝታው ከነበረው ከእውነተኛው እንጨት ላይ ተቆርጦ የመጣ ነው ተብሎ በኢትዮጵያ ነገሥታትና ሊቃውንት ዘንድ የከበረና እንደ ብርቅ የሚታይ ነው ። በቤተ መንግሥቱ አልማዝና ወርቅ ከአልማዝና ከወርቅ የተሠራም ሌላ ገጸ በረከት ሳይጠፋ ይኸንን የእንጨት መስቀል አሠርተው መላካቸው የፖርቱጋልን ንጉሥ ከዚህ የበለጠ የሚያስደስተው ነገር እንደሌለ ፣ በሌላው በወርቅና በአልማዝ በጥር ሀብት ራሱ በጣም የከበረ መሆኑን ገምተው ይሆናል ። በዚህም ላይ የዝምድናው ዋና ምክንያት የክርስቶስን ሃይማኖት በመከላከል እስላሞቹን ለመቃወም ስለሆነ በዚህ ዓይነት ለሚፈለገው ዝምድና የጌታችንን መስቀል መላክ ለጉዳዩ ተስማሚና መልካም ምልክት (SYMBOLE) ነው ብለው አስበው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ከዚህ በፊት እንዳልነው የፖርቱጋል ንጉሥ ፕሬስቴ ጆአአ (ቄስ ዮሐንስ) በሚባል ፍጹም ክርስቲያን በሆነ ንጉሥ የሚመራ የኢትዮጵያ መንግሥት አለ ማለትን ከኢትዮጵያና ከኢየሩሳሌም የሚሔዱ ሰዎች እያመጡ ወሬውን ሲሰማ የነበረውን አገር አሁን መልክተኛው ምንም አርመን ሆና የውጭ አገር ተወላጅ ቢሆን በጣም ደስ ብሎት በክብርና በደስታ እንደተቀበለው በየመጽሐፉ ተገልጿል ። ነገር ግን ይህ ሰው ዘሩ አርመን ቢሆንም ሃይማኖቱ ተዋሕዶ ከብዙ ዘመን ጀምሮ በቤተ መንግሥቱ ያገለገለ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መኰንን የሚቆጠር መሆኑን ንግሥቲቱ በደብዳቤያቸው ላይ ገልጸውታል ። በዚህም ላይ ይኸን ለመሰለው መልእክት የውጭ አገር ያላየ ፣ የውጭ አገር ቋንቋና ሕይወት የማያውቅ ኢትዮጵያዊ መኰንን ከመላክ እርሱን መላካቸው ለነገሩ ተስማሚ ሰው መፈለጋቸውን ያስረዳል ። ይህም ሰው ባለፈው እንደተመለከትነው ሃይማኖቱ ክርስቲያን አገልጋይነቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ ለጉዞ እንዳይቸገር የተፈረከገ ዜግነት ደርቦ በመያዝና ጉዞው በነጋዴነት መልክ ነው ።

ንግሥት እሌኒ በዚህ ደብዳቤያቸው ላይ «ከትልቁ የጦር አሊቃህ ከትሪስታን ደ ኩኛ ዘንድ አንዱ ዮሐንስ ቄስ ነኝ የሚል አንዱ እንደርሱ ንጉዝ ተብሎ የተሠየመ ሁለት መልክተኞች ወደኛ መጥተው . . . . .» ይላል ። ትሪስታን ደኩንሃ (TRISTAN DA CUNHA) የሚባል የታወቀ የፖርቱጋል መርከበኛ የጊዜ ወደ አፍሪካ የመጣ አለ ። ይህ የጦር መኰንን በዋናው የጦር አዛዥና በንጉሡ እንደራሴ በአልፎንሱ ደ አልቡኬርክ (Alfonsu d'alhukerque) ትእዛዝ እንደ ኢ. አ. ፲፭፻፲ ዓ. ም. ላይ እነዚህን ሁለት መላክተኞች ይዞ የመጣው መሆን አለበት ። ንግሥት እሌኒም ይኸን ደብዳቤና ማቴዎስን ለመላክ ያሰቡት ዋነኛው ምክንያት እነዚህ

ISIC

ሁለት መልክተኞች ከመጡ በኋላ ነው (1) ።

ቀጥሎ «ወደ ኢየሩሳሌም ቁስ ስንልክ በሚባርከን በፓትሪያርክ ማርቆስ ፈቃድ መላክተኞችንን ማቴዎስን ወዳንተ ላክሁት . . . . ፓትሪያርክ ማርቆስ የኛና ያገራችን ሁሉ መንፈሳዊ አባት ናቸው» የሚሉት የየትኛውን አገር ፓትሪያርክ ነው እንዳይባል በዚህ ዘመን ከ፲፬፻ ጀምሮ እስከ ፲፮፻ ዓ.ም. ድረስ ማርቆስ የሚባሉ ፓትሪያርክ በእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ አልተቀመጡም ። በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ፺፬ኛ ፓትሪያርክ አባ ዮሐንስ ፲፫ኛ ናቸው ። እርሳቸውም በሥልጣን የነበሩበት ጊዜ ፲፬፻፹፬ - ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. እ. ኤ. አ. ነው ። ስለዚህ ካዜ ናዖድ ጊዜ ጀምረው የኢትዮጵያ ጳጳስ የነበሩትን በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የሚቀመጡትን ግብጻዊውን ጳጳስ አባ ማርቆስን ማለታቸው ለመሆኑ ጥርጥር የለበትም ። ምናልባት በግዕዝኛ ደብዳቤ ላይ ንግሥቲቱ የኢትዮጵያ ጳጳስ ያሉትን ከግዕዝ ወደ ፖርቱጋል ከዚያም ወደጥንቱ ፈረንሳዊኛ ሲተረጉም ጳጳስ የሚለውን ቃል ፓትርያርክ ብለው ተርጉመውት ይሆናል ። አንድ አንድ ጊዜ የዚያን ዘመን ጸሐፊዎች የቤተ ክህነትን የማዕርግ ስም መለየት እያቃታቸው ጳጳሱንም መምህሩንም ፓትርያርክ ብለውት ይገኛል ። ወደፊት እንደምናነበው ዓረብ ፋቂህ የሐይቁን መምህር ፓትሪያርክ ብሏቸው ይገኛል ።

ንግሥት እሌኒ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ማቴዎስን ለመላክ የጳጳሱን ፈቃድ ያስፈለገበትን ምክንያት ምንድነው ብለን ራሳችንን የጠየቅን እንደሆነ መልሱ ሁለት ባሕርይ ከሚለው ከካቶሊክ ንጉሥ ጋር ለመቃረብ ለመዛመድና ለመጋባት ሲፈለግ ከካህናት በኩል የሐሜታና የወቀሳ ነፋስ መነሣቱ ስለማይቀር የጳጳሱን ፈቃደኛነት አስገብቶ በዚያ በኩል የሚነፍሰውን ወቀሳ ለማገድ ይሆናል ። ወይም ለዚህ ዝምድና ቤተ መንግሥቱም ቤተ ክህነቱም መተባበሩን ለፖርቱጋል ንጉሥ ለመግለጽ ይሆናል ።

ጳጳሱ አባ ማርቆስም ምንም ዘራቸው ግብፃዊ ዜግነታቸው በዚህ ዘመን የነበረው የሱልጣን እል ጋውሪ (፲፭፻፩ - ፲፭፻፲፮ ዓ. ም.) ቢሆን በሃይማኖታቸውና በመንፈሳዊ አባትነታቸው ምክንያት ክብርም ጥቅምም ለተጐናጸፉባት አገር ለኢትዮጵያ ደኅንነት ሲሉ ከንግሥት እሌኒ ጋር በማበር የፖርቱጋልንና የኢትዮጵያን ዝምድና መደገፋቸውን እንመለከታለን ።

ንግሥቲቱ «አገራችን ግዛታችን የሚገኘው ከባሕር ርቆ በየብስ ስለሆነና ወደብ ስለሌለን የባሕር ጦር ለማደራጀት አልቻልንም ። መርከበኛ ወታደርም የለንም» ማለታቸውን እንብበናል ። መቼም የምጥዋ ወደብ ከአክሱም መንግሥት ዠምሮ የኢትዮጵያ ወደብ መሆኑ አይጠረጠርም ። ከአክሱም ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት ራሱ በዓረቦች ባይወረርም ከዚህ በፊት እንዳልነው ከቀድሞው ኃይሉና ሥልጣኑ ዝቅ ብሎ በመዳከሙ ወደቦቹን ለመያዝና በዚያ በቀጥታ ሸቀጥ ለመላክም ለመቀበልም በባሕር የሚመጣውን ጠላትንም ለመቆጣጠር አልቻለም ማለት ነው ።

(1) A.H.M. Jones-E-Monroe የጳፉት የሀበሻ ታሪክ ገጽ 88

ስለዚህ በዚህ ጊዜ ግብፆች ከኢትዮጵያዊው ገዥ ከባሕር ነጋሽ በመርከብ እየ መጡ ምጥዋንና አካባቢውን እየነጠቁ እጅ ማድረጋቸውን ወደፊት እንደምናገኘው ፡ የፖርቱጋል ወታደርም በመርከብ እየመጣ ከነርሱ እጅ በውጊያ እየተማ እጅ ማድ ረጉንና ከባሕር ነጋሢያችን ጋር መነጋገሩን እንመለከታለን ። ባሕር ነጋሢውም ያገር ተወላጅና ባላባት እንደመሆኑ መጠን በጦር ኃይል በመርከብ እየመጡ ወደ ቡን የሚነጥቁትን ግብፆች ሳይመቸው ወደኋላው ወደ እገሩ እየሸሸ ሲመቸው ወደ ፊት እየገፋ እያደባ በግብፆች ላይ አደጋ እየጣለ እንደሚያስቸግራቸው የታወቀ ነው ። እንደዚሁም ሃይማኖታቸው እስላም የሆነው በምጥዋ አቅራቢያ በቀይ ባሕር ደሴት ውስጥ ያሉት ባላባቶችና የአርኪቆው ባላባቶች "ናይብ" ጊዜ ባነሳ ውና ኃይል ባገኘው አንድ ጊዜ ለኢትዮጵያዊው ለባሕር ነጋሽ አንድ ጊዜ ለግብ ፆች እየተገዙ ቆይተው በመጨረሻ ደግሞ ቱርኮች በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ድል አድርገው ግብፅን ከያዙ ወዲህ እንደዚሁ ለቱርኮቹ እየተገዙ ፡ ደግሞ በኋላ በ፲፭፻፺፪ ፡ ግድ ላይ ፖርቱጋሎቹ ቱርኮቹን አባርረው ምጥዋ ሲገቡ እነርሱን ማስተናገዳቸው የታወቀ ነው (1) ። በራሱ ለመቆም ኃይል የሌለው ሁሉ ሊላውን አሸንፎ ኃይለኛ ለሆነው መገዛት በየትኛውም የዓለም ክፍል የተለመደ ስለሆነ የምጥዋ የአርኪቆ የቱአኪም የእስላም ያገር ባላባቶች በየጊዜው ጌታ ቢለዋውጡ ሊፈረድባቸው አይችልም ።

ISIC

## ምዕራፍ ፲፪
## ስለ አፄ ልብነ ድንግል

ካፄ ልብነ ድንግል በፊት የኢትዮጵያ ሁኔታ ምን እንደነበረ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚባለው ፪ኛ መጽሐፍ ተጽፏል ። በዚህም ጽሑፍ ውስጥ ጠቅላላ ሙሉ ታሪክ ሆኖ ሊገባ የሚገባው የኤኮኖሚ ፡ ያስተዳደር ፡ የብሔራዊ ሙኑ የተጻፈ ዝርዝር ታሪክ ካለመገኘቱ የተነሣ አብዛኛው ጊዜ በየጽሑፉ ውስጥ የሚነበበው የነገሥታቱ በዙፋን መከታተል በዘያው በዜና መዋዕሉና በውጭ ሕይወት አኗኗር ፡ የጤና አጠባበቅ ፡ የወታደር ድርጅት ፡ የፍርድ አሰጣጥ በየዘ አገር ጸሐፊዎች የተገኘው የጦርነት ታሪክ ነው ። እስኪነግሥ ድረስ ያለውም የነጋ ሚው የግል የሕይወት ታሪክ አይገኝም ። ምክንያቱም ንጉሡ የራሱን ታሪክ በጸ ሐፊ ትእዛዙ በኩል የሚያጽፈው አብዛኛ ጊዜ ከነገሠ በኋላ ያለውን ነው ። ስለ ዚህም ዓፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ አህመድ ጦርነት በፊት የነጋሢነት ሥልጣን በሙሉ ከመጨበጣቸው በፊት ያለው የግል አስተዳደጋቸው ዝርዝር የለንም ።

የአስተዳደጋቸው ዝርዝር ታሪኩ ባይገኝም የመንፈሳውያኑና የሊቃውንቱ የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የዓፄ ናዖድ ልጅ ስለሆኑ መንፈሳዊ ትምህርት እየ ተማሩ ያደጉ መሆናቸው አይጠረጠርም ። በፊተኛው ምዕራፍ እንዳመለከትነው

(1) Verdadeira in Formaçao Das Terras do preste Joao የሚባለው የፍራንቸስኩ አልቫሬዝ መጽሐፍ ምዕ. 2



የዐፄ ናዖድና የልጃቸው ያፄ ልብነ ድንግል በዲማ ጊዮርጊስ የሚገኝ ስዕል ። ስዕሉ በዘመናቸው ካሉት ፈረንጆች ባንዱ ምናልባትም በብራንካ ሌዎን እጅ የተሣለ ሳይሆን አይቀርም ፤ (ፎቶ ሽኔይደር)

በኢትዮጵያ የዘመኑ ሊቅ የሚያሰኘው ትምህርት ያው ብሉይና ሐዲስ ሊቃውንት የሚባለውና ይኸንኑ የመሳሰለው ስለሆነ እርሳቸውም እንደባቶቻቸው በመንፈሳዊ ትምህርት ማደጋቸው አይጠረጠርም ።

ፖርቱጋሎች የዚህን ዘመን ንጉሥ በጠቅላላው (PRESTE JOAO) ቄስ ዮሐንስ እያሉ የሚጠሩበት ምክንያት የንጉሡን የመንፈሳዊ ዝንባሌ ወደ ኢየሩሳሌም ከሚሄዱ የኢትዮጵያ ምእመናን በመስማት መሆን አለበት ። የዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደ ጳጳስና እንደ ቄስ በእጁ መስቀል ይይዝ እንደነበረ በየመጽሐፉ ይነበባል ። ዓፄ ልብነ ድንግል በመንፈሳዊ መጽሐፍ ሊቅ እንደነበሩ የምንረዳው በግዕዝ የተጻፈው ታሪከ ነገሥት ልጆቻቸውን ግላውዴዎስን ከሌሎች ልጆቻቸው ለይተው ማስተማራቸውን ራሳቸውም ሊቅ መሆናቸውን ለመግለጽ እንደዚህ ይላል «አባቱ ከወንድሞቹ የበለጠ የቅዱሳት መጻሕፍትን ዕውቀታቸውን (ኃይላቸውን) ያስተምረው ነበር ። እርሱ ራሱ (ልብነ ድንግል) ታላቅ ብልህ ስለሆነ የመጻሕፍት የላይ ንባባቸውን የውስጥ ምሥጢራቸውን ስለሚያውቅ አስተማሪ ሆነው . . . . . .» (1) ። በዚህ ምክንያት ጊዜያቸውንም ከሊቃውንት ጋር በመንፈሳዊ ክርክር ያሳልፉ ነበር (2) ።

በየጊዜው በየቋንቋው የተጻፈው አጭሩ ያገራችንና የውጭ አገር ጽሑፍ እንደሚያስረዳን አፄ ልብነ ድንግል [sic] የዓፄ ናዖድ ልጅ ፣ የዓፄ በዕደ ማርያም የልጅ ልጅ ናቸው ። አፄ በርግ ያዕቆብም ቀድሞ አያታቸው ናቸው ። አፄ ናዖድ ፲፫ ዓመት ገዝተው ሲሞቱ በ፩ሺ፭፻፱ ዓ. ም. አፄ ልብነ ድንግል ገና የ፲፩ ዓመት ወጣት ሳሉ ስለነገሡ እንደ አባታቸውና እንደ ቀድሞ የነገሥታት ልጆች የአምባ ግሺንን የግዞት ኑሮ አልቀመሱትም ። የዚህንም ምክንያት በሁኛው መጽሐፍ ባፄ ናዖድ ዘመን መንግሥት ላይ ገልጸናል ። የንጉሡት በተወለዱ በአሥራ አንድ ዓመታቸው ከሆነ የተወለዱበት ዓመት ፲፬፻፺፱ ዓ. ም. ይሆናል ።

ስመ መንግሥታቸው ወናግ ሰገድ መሆኑ ወናግ ማለትም በሐረርጌዎችና በውጋዴን ቋንቋ አንበሳ ማለት መሆኑ በየመጽሐፉ ተጽፏል ። የግዕዙንና የአማርኛውን ቋንቋ "አንበሳ ሰገድን" ትተው በውጋዴንና በሐረርጌዎች ቋንቋ ወናግ ሰገድ የተባሉበት ምክንያት ምናልባት ያን ጊዜ በደፋትና በፈጠጋር ያለውን ግዛት የሚያውኩ ያዳልና የሱማሌ ተወላጆች ስለሆኑ እነርሱ በሚያውቁት ቋንቋ ተሰይሞ ለማስፈራራት ይሁን ወይም የነርሱ ገዥ ጭምር መሆናቸውን ለማስታወቅ ይሁን ወይም የሱማሌው ቋንቋ በርካቶ ብዙ ጊዜ በአማርኛው ውስጥ እየገባ በመነገሩ ይሁን አይታወቅም ። ወደፊት በታሪካቸው ውስጥ እንደምናገኘው የፈጠጋር

(1) ያሌብዖ አቡሁ ኃይሎን ለመጻሕፍት ቅዱሳት እም እንቂሁ ፈድፋደ እስመ ውእቱ በዓለ ልቡና ዓቢይ ወአቡሁኒ ኮነ ማዕምረ አፍአሆሙ ወውሳጢሆሙ ለመጻሕፍት ስለ ገዢ ኮነ ሎቱ መምህረ ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 97

(2) ወንጉሥሰ መሢሐዊ ልብነ ድንግል በውእቱ መዋዕል ረሰየ ሎረቶ ኀበ እንግሊዝ መጻሕፍት . . . ሕገ መንፈሳውያን ወም ሶበኒ ይትፌሣሕ ይጸሐፉ ከሀናት ወይዘዋዕ ምስሌሆሙ በንገረ መጻሕፍት . . . ኮ ሮሰኒ ያ/ ተመው ታሪካቸው ገጽ 8 ።




ዓፄ ልብነ ድንግል በዘመናቸው ያጻፉት የተአምረ ማርያም ያንዱ ምዕራፍ መጨረሻ የብዕሩ አጣጣል በጣም ያምራል ። ሥዕሎቹ ባንድ የውጭ አገር ተወላጅ የተሳሉ ይመስላል ። ሥዕሉን በፎቶ ከተድባበ ማርያም ያነሡት ማዳም ስፔንሰር ናቸው ።

አገረ ገዥ ራስ እስላም ሰገድ (አንዳንድ ጊዜ ባሜሩ እዝማች እስላሞ) ይባል ነበር ። የዚህ ዓይነቱም ስያሜ ከልጅነት ከአባትና ከናት የተሰጠ ስያሜ ሳይሆን ሰውዩው አድጎ ከእስላሞች ጋር ተዋግቶ ድል ባገኘ ጊዜ የሚሰጥ የፈረስ ስም ዓይነት ነው ። የፈረሱ ስምም ውሎ አድሮ መጠሪያ ስም ሆኖ ይቀራል ።

ይኸም ስያሜ አንዳንድ የጦር አለቆች ዓረብ አስፈሬ ፡ አዳል አስፈሬ ይባሉ ከነበረው ጋር ሊመሳሰል ይችላል ። ይግም "አንበሳ በጦር" ተብለው አባትየው ናዖድ ስለ ተሠየሙበት በትርጉም ቢቀር በአጠራሩ እንዲለያይ አንበሳ ሰገድ በመ ባል ፈንታ ወናግ ሰገድ ተብለው ይሆናል ።

ወደፊት እንደምናገኘው አፄ ልብነ ድንግል ራሳቸው ለፖርቱጋል ንጉሥና ለሮማ ሊቀ ጳጳስ በጻፏዋቸው ደብዳቤዎች ላይ "ስሜ ልብነ (ዕጣን) ድንግል ፡ ትር ጓሜውም ድንግል ያበራችለት ፡ ይኸም ስም የተሰጠኝ ቅድስት ጥምቀትን በተቀበ ልሁበት ቀን ነው ። በነገሥሁ ጊዜ ደግሞ ዳዊት ተባልሁ" የሚል ቃል ስለአለበት "ዳዊት" የተቀደሰ ስነ ጽሑፍን የተደገፈ ስመ መንግሥት ወናግ (አንበሳ) ሰገድ ደግሞ ወታደራዊና ከሕዝብ የተሰጠ የፈረስ ስም ይመስላል ። ስለዚህ ታሪከ ነገሥቱ "ወስመ መንግሥቱ ወናግ ሰገድ" ያለውን እርሳቸው "በነገሥሁ ጊዜ ዳዊት ተባልሁ" ብለው ያስተባበሉበት ምክንያት በዚህ አኳይ በስጠነው ምክን ያት ሳይሆን አይቀርም ። በጸሐፊ አለማጣራት ምክንያት ብዙ ጊዜ የነገሥታት መጠሪያ ስም የክርስትና ስም የመንግሥት ስም ብዙ ጊዜ እየተለያየ በመጻፍ ያደና ግራል ።

ስለ ዕድሜታቸውና ስለመልካቸው ዝርዝር ሁኔታ ማግኘት ችግር ነው ። ነገር ግን የፖርቱጋል መንግሥት በንጉሡ በ፲፱ኛው ዓመት የላካቸው መልእክተኞች ፍራ ንቼስኮ አልቫሬጽና ዶም ሮድሪግ እ. አው. አ. ፲፭፻፳ ዓ. ም. ከሕገድ በምጥዋ በኩል መጥተው የተገናኙዋቸው ጊዜ «ቁመታቸው መካከለኛ ፡ ዕድሜያቸው ፳፫ ዓመት ፡ ጥቁር ያልሆነ ፈካ ያለ ቀለም የአላቸው ። መልካቸው ክብ ብሎ ክብ የሆነ መብቀል የገመረ ሆኖ ምንም ዕድሜያቸው ወጣት ቢሆን ከበድ ያለ የባለሥልጣን ጌታ መልክ ይታይባቸዋል» ብለው ጽፈዋል (1) ።

የሆን ሆኖ ዓፄ ልብነ ድንግል በ፲፭፻፰ ዓ. ም. በተወለዱ በ፲፩ ዓመት ሲነግሡ
በመንግሥቱ ሥራ እናታቸው ናዖድ ሞገሳ ያያታቸው ያዒ በእይ ማርያም ባለቤት
ንግሥት እሌኒ እንደዚሁም ራስ ወሰን ሰገድ በሞግዚትነት ያግዟቸው ነበር (2) ።
ዓፄ ልብነ ድንግል ከሞግዚትነት ሥር ወጥተው በቀጥታ የመንግሥቱን ሥል

(1) Fernao lopes de Castanheda (1551) "Historia do descormen to ... በሚል አርእስት ከጻፈው ውስጥ የፖርቱጋል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደ ፈረንሣይ አስተርጉሞ በ፲፱፻፷፬ ዓ ም ካሳተመው ላይ ምዕ 10 ገጽ 142 ።

(2) ወአሜሃ ትትሜጣበ መንግሥት በትእዛዘ ወላዲቱ ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ፡ ወበምክረ ካልእት ንግ ሥት እሌኒ እስመ የአምራ ሠሪዓ ቤተ መንግሥት ፡ ወፈድፋደሰ ዛቲ ጠባብ እሌኒ ተአምር ሕገ መንግሥት ..... በምክረ ጠቢብ ወለባዊ ወሰን ሰገድ በዓለ ዳግም .... የልብነ ድንግል ታሪከ ነገሥት ሮሲኒ ያሳተመው ፤ ገጽ 6 ።

ጣን የጨበጡበትን ትክክለኛ ጊዜ ማወቅ ችግር ነው ። እነዶም ሮድሪግ ከፖርቱ ጋል ተልከው መጥተው እ.አው.አ. ፲፭፻፳ (እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ፲፭፻፲፪) ላይ የተገናኙዋቸው ጊዜ ዕድሜያቸው ፳፫ ዓመት ስለሆነ ምናልባት ሙሉ ሥልጣ ንን በ፲፫ ዓመታቸው ይዘው ይሆናል ። ይኸውም ዘመን ፲፭፻፩ ዓ. ም. ይሆናል ። አልቫሬዝ ደግሞ በምዕራፍ ፩፻፲፩ ላይ በበኩሉ ልብነ ድንግል ከማኅፉድ የተዋጉ ጊዜ ዕድሜያቸው ፲፯ ዓመት ነበር ስለሚል ምናልባት የመንግሥቱን ሥልጣን ከ፲፯ ዓመታቸው ጀምረው ይዘው ይሆናል ። ነገር ግን የማኅፉድ ጦርነት የተደረ ገው በ፲፭፻፳፭ ዓ. ም. ስለሆነ በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸው ፲፱ ቢያንስ ፲፰ ዓመት መሆን ስለአለበት ከአልቫሬጽ አጻጻፍ ጋር ምንም ያህል አልተራራቀም ።

አፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥታቸው በተድላና በደስታ ዠምሮ በኀዘንና በስደት የተፈጸመ መሆኑን በመንግሥታቸው መዠመሪያ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በይፋት ከእስላሞቹ ባላባት ከይማም ማኅፉድ ጋር ተዋግተው ድልን ከተጐናጸፉ በኋላ በመጨረሻው በግራኝ አህመድ ተሸንፈው ከአውራጃ ወደ አውራጃ እየተሰደዱ ኖረው በመጨረሻ ሞተው ደብረ ዳሞ መቀበራቸውን ወደፊት በዝርዝር እናነባ ለን ። ሥልጣን ከመጨበጣቸው በፊት በንግሥት እሌኒም አማካይነት ራሳቸውም በቀጥታ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ያደረጉት ወዳጅነት ለጊዜው በእስላሞቹ በኩል ያለውን ጠብ አጣደፈው እንጂ ከመወረር ሊያድናቸው አልቻለም ። ቱርክና ዓረቦች ከቅርቡ ለግራኝ አህመድ ሲረዱ ፖርቱጋል ከኢትዮጵያ በጣም ከሚር ቀው ከገዛ አገሩ ከፖርቱጋልና ከግዛቱ ከሕንድ በመዠመሪያዎቹ የወረራ ዘመኖች ለመርዳት አዳግቶት የጦርነት መከራና ሥቃይ ፲፬ ዓመት ሙሉ በኢትዮጵያ ላይ ጸንቶ ቆየ ።

ዓፄ ልብነ ድንግልን በቅርብ ያያቸውና ብዙ ጊዜ ያነጋገራቸው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ የጻፈውን"VERDADEIRA"እውነት የሚባለውን መጽሐፍ ስናነብ ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ በ፳፫ - ፳፬ ዓመት የወጣትነት ዕድሜያቸው ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት የሚያደሉ መጻሕፍት ወዳድ ፣ የውጭን አገር የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሥነ ሥርዓት ወግና ታሪክ ለማወቅ በጥብቅ የሚመራመሩ እንደነ በሩ ያስረዳል ። ለነአልቫሬጽ የራሳቸውን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ወግና ሥርዓት ካሳዩት በኋላ "ከኛና ከናንተ ከፖርቱጋሎች የማን ይበልጣል ወይም ይሻ ላል እደራህን ሳትደብቅ ንገረኝ" እያሉ መጠየቃቸው ባንድ ወገን በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ከፍ ያለ የሥልጣኔና የኑሮ ደረጃ ልዩነት አለመረዳታ ቸውን ባንድ ወገን ደግሞ ይኸን ካወቁ በኋላ የመሻሻል ምኞት እንደነበራቸው ያሳ ያል ። የጦርነት ጊዜና ሞት ቀደማቸው እንጂ አገራቱንም ለማሠልጠን ምኞታ ቸው እንደነበረ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ ፫ኛ ከጻፉት ደብዳቤ ላይ ወደፊት እንገነዘባለን ።

ይኸው አልቫሬጽ በጻፈው መጽሐፍ ላይ የመልእክተኞቹ መሪ ሮድሪግ ጳጳ ሱን አቡነ ማርቆስን አስፈቅዶ የተገናኛቸው ለት "ንጉሠ ነገሥቱ መልካምና ቅዱስ ሰው ነው . . በክርስትና ሃይማኖት ያለው እምነት የማይበገር ነው" ሲሉ

እንዳሜወቱት ገልጸታል (1) ። ይልቁንም ባለመበገር ረገድ ንጉሡ ያላቸውን ግትር ጠባይ ያሜወቱት ትክክለኛ መሆኑን የምንረዳው የግራኝ አህመድ ወረራና መከራ በዕድል እንደቀጠሮ በጊዜያቸው ደርሶ ጠላታቸው በየጊዜው ከድል ወደ ድል እየተራመደ አገራቸን በወረረበት ጊዜ ፲፬ ዓመት ሙሉ ያን ያህል የጦርነት የመከራና የስደት ውርጅብኝ ሲጫናቸው ከወለዷቸው ልጆች መካከል ፊቅጦር በጦርነቸ ሲሞት ፥ ሚናስ ከብዙ ንጉሣዊ ቤተሰብ ጋር ሲማረክ አንድ ቀን የትግል አሳባቸውን ለውጠው የመላላትና ከጠላታቸው ጋር የመታረቅ መንፈስ አሳይተው አያውቁም ። "ከእጅ የማያድንህ የለም ይልቅስ ሴት ልጅህን ላርልኝና በመካከላችን ሰላም ይውረድ" ብሎ ዘወትር ጦርነቱ የሚቀናው አሸናፊ የሆነው ግራኝ አህመድ የጠየቃቸውን እምቢ እንዳሉና ንጉሡ ነገሥታዊ ክብራቸውን እንደተጐናጸፉ በዚህ ጊዜ (፲፭፻፲፱ - ፲፭፻፴፪ ዓ. ም.) መከራና ስደት ካጠቃት ካገራቸው ከኢትዮጵያ ከሚወዷቸውና መከራና ስደቱን በብርታት ከሚካፈሏቸው ባለቤታቸው ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል በሞት ተሰናብተው ደብረ ዳሞ ተቀበሩ ፡ ዝርዝር ታሪኩን ወደፊት በየሥፍራው እናነባለን ።

በኝህ በመከረኛ ንጉሥ ላይ የምንሰነዝረው ፍርድ ሁለት ዓይነት ነው ፡

፩ኛ. በግራኝ አህመድ ዋዜማ ፥ የራሳቸው መንግሥት በቅድሚያ ዝምድናውን ፈልጎ ከፖርቱጋል ንጉሥ 1527 ከአማኑኤልና ከሕንዱ እንደራሴ ዘንድ ተልከው የመጡትን በቶሎ ተቀብለው በለአገር የሚበጀውን ተነጋግረው አስደስተው በመላክ ፈንታ ከወር በላይ ተቀብሎ ለማነጋገር ደጅ ማስጠናታቸውን ፡ በዚሁ ጊዜ የጦርነትና የፖለቲካውን ጉዳይ የያዘውን ዋናውን የመልእክተኞቹን ሹም ሮድሪጎ ዴ ሊማን በውጭ አስቀምጠው የቤተ ክህነቱን ሰውዬ ፍራንቼስኮን በየቀኑ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ግቢ በመጥራትና ስለ ቅዳሴ ስለማኅሌት ስለ ቅዱስ ቁርባን ስለ መሥዋዕት ስለ ንዋየ ቅድሳትና አለባበስ ሲነጋገሩ መሰንበታቸውን ስንመለከት ፤ በዚህ ዓይነት ቸልታ ከዓመት በኋላ በርሳቸውና ባገራቱ ላይ የደረሰውን ጦርነት ሊመልሱ የሚችሉበትን የመሣሪያና የወታደር ትጥቅና ድርጅት ሳያበጁ በመቅረታቸው ይነቀፋሉ ።

፪ኛ. ወደፊት በዝርዝር እንደምናነበውና እላይ እንዳልነው የሰላሙና የመዘጋጀቱ ጊዜ በዋዛ ፈዛዛ አልፎ ጦርነቱ መከራው በበዛበት በረዥም ጊዜ ውስጥ ያላውሉ መመከታቸውን ስናይ የፈተኛው ጉድለት ያስከተለው ነቀፋ ተመልሶ ይሸራል ። ባይሻርም ጐን ለጐን ሆኖ የሰጡን ጉድለቱንና ምላቱን ያሳያል ።

በታሪክ ውስጥ ሊደነቅ ሊመሰገን የሚገባው በጦር ሜዳ ተዋግቶ አሸናፊነትን የታደለ ብቻ መሆን የለበትም ። ነገር ግን በመሣሪያና በአወጋግ ዘዴ ልዩነት በጠላት እንዲጋጣሚ ዕድል እጥቶ የተሸነፈና በስደት የሞተ መሪ የሚታየው ጽኑ

(1) የአልቫሬዝ መጽሐፍ ምዕ. 103

መንፈሱና ያወዳደቁ ፍጻሜ ስለሆነ በታሪክ ፊት ለዚሁ ተመጣጣኝ ክብር ሊነፈግ
አይገባም ።

ድል ማድረግና ድል መሆን አንዳንድ ጊዜ በአጋጣሚ ይደርሳል ። ነገር ግን
እርሳቸው ቢሞቱም ከመሞታቸው በፊት በርሳቸውና በእንጀራ አያታቸው በንግ
ሥት እሌኒ አማካይነት ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር በተወጠነው የወዳጅነት ግን
ኙነት ምክንያት የፖርቱጋሎች ርዳታ ለልጃቸው ላዔ ገላውዴዎስና ለባለቤታ
ቸው ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል ደርሶ ኢትዮጵያን ከወረራ አድኗል ።

ስለዚህ ከጦርነቱ በፊትና በዋናው የግራኝ ጦርነት ዋዜማ ከግብጽ ጋር የነበረ
ን ሁኔታ ፤ የግብፅን በቱርክ መወረር ፤ የኤሚር ማኅፉድን ባዔ ልብነ ድንግል
መሸነፍ ከፖርቱጋል ንጉሥ ከአማኑኤል ዘንድ ስለመጡት መላክተኞች ከማንበባ
ችን በፊት ስላዔ ልብነ ድንግልና ስለእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋብቻ እናንብብ ።

## ምዕራፍ ፲፫

## የአፄ ልብነ ድንግልና የእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋብቻ

የዓፄ ላሊበላ ባለቤት በመጠሪያ ስሟ በመስቀል ክብራ ላይ በዓልተ ቢሐት (የቢ
ሐት እመቤት) እየተባለች እንደ ማዕርግ ስም እየተጨመረ መጠራቷን ገድለ ላሊ
በላ የሚባለው መጽሐፍ ያመለክታል (1) ።

ይህ ንጉሥ እንደዚሁም ከርሱ በፊትና ከርሱ በኋላም ያሉት የዛጉዌ ነገሥታት
ካንድ ሚስት በላይ ሁለት ሚስት ማግባታቸውን በጽሑፍ አልተመለከትሁም ።
መንግሥት ከዛጉዌ ወደ ይኩኖ አምላክ ከዞረ በኋላ እስከ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ያሉት
ዘጠኝ ነገሥታት ባንድ ሚስት ይወሰኑ ወይም ብዙ ሴት ባንድ ጊዜ ያግቡ የሚገ
ልጽ ጽሑፍ የለም ። ስለነርሱ የተጻፈ ዝርዝር ታሪክ በጽሑፍ ተጽፎ ወደ ጊዜያችን
የተላለፈ ባለመኖሩ በግልም በመንግሥታዊ ደረጃም የፈጸሙት ሁሉ በሙሉ አይታ
ወቅም ።

አሥረኛው ንጉሥ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ግን ታላቂቱ ንግሥት ዠን መንግሣ የም
ትባልና ታናሺቱ ንግሥት የሚባሉ ሁለት ሚስቶች እንደነበሩት ከነሐቀዲን ጋር
ያደረገው የጦርነቱ ታሪክ ያረጋግጣል ። ይኸው ንጉሥ ከሁለት በላይ ሚስቶችና
ዕቁባቶች እንደነበሩት ለማስረዳት ታላቂቱ ንግሥት በኋላው ተከትላው ወጣች
ካለ በኋላ ሌሎችም ንግሥታትና ዕቁባት አብረው ወጡ ይላል ። እልፍ ብሎ ደግሞ
"ትንሺ ንግሥት ታላቂቱን አነጋገረቻት" ይላል (2) ።

ከነዚህ ውስጥ እንደኛዪቱ ያባቱ ያዔ ውድም ረዓድ ሚስት ስለነበረች በዚህ

(1) Evangelo d'oro di Debre Libanos-Conti-Rossini ገጽ 16
(2) ንግሥት ወጽአት ካዕበ እንተ ድኅሬሁ ወካልዓት ንግሥታት ወዕቁባት ወጽአ . . . . . ወትቤላ
ንግሥት እንተ ትንእስ ለእንተ ተዓቢ . . . . . ያዔ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ዡል ፔሩሾ ያሳተ
መው ገጽ 388 - 389

ምክንያት እንደሌት ያባትህን ሚስት ታገባለህ ? የማትወልደኝ ከሆንች ምን አለበት በመባባል በዚህ ንጉሥና በዘመኑ እጨጌ በእቡነ ፊልጶስ መካከል የተነሣውን ከፍ ያለ ጠብ በዚሁ ጠብ የተነሣ በፊልጶስና በተከታዮቻቸው በነአባ አኖሬዎስ ላይ የደረሰውን ግርፋትና ስደት ከገድለ ፊልጶስ ላይ በሰፊው ተተርኮ የሚገኘውን ባለፈው አመልክተናል ።

ከርሱ ወዲህ የተነሡት ነገሥታት እነ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፥ እነ ዓፄ በዕደ ማርያም ቀኝ በዓልተሐት (የቀኝ ባለቤት) ግራ በዓልተሐት (የግራ ባለቤት) እያሰኙ ሁለት ሁለት የሴት ንግሥታት በወግና በሥርዓት ሥርዓተ ንግሥ እያስፈጸሙ ያገቡ ነበር ። አንዳንድ ጊዜም ''በዓልተ ሽሁና አንዳንድ ጊዜ በዓልተ ሽሁና'' እየተባለች ሦስተኛ መጨመሯ በበዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ላይ ይገኛል (1) ።

እንደ ክርስቲያን ንጉሥ ባንድ ሴት በመወሰን ፈንታ ከዚያ አልፈው ሁለት ሚስት ማግባታቸው ዕቁባት ማስቀመጣቸው የራሳቸው የሥጋ ፍትወታቸው ከሚጠይቃቸው አልፎ ሌላ ምክንያት አለ ። እንደኛው ነገሥታቱ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ታላላቅ የአውራጃ ባላባቶች ከደዋሮውና ከሐድያው ገራዶች ሲጋቡ በዚህ የፖለቲካ ጋብቻ የአውራጃውን ባላባት በነርሱ ላይ እንዳያነሣ በጋብቻ ዝምድና ያስሩታል ። ሁለተኛው ምክንያት እያንዳንዱ ንጉሥ በዙፋኑ የሚከተለው ልጅ እንዲኖረው ምኞቱ ስለሆነ ፩ኛይቱ መካን ስትሆን ሌላዋ በመውለድ ዘር እንድታተርፍለት ፤ ካንዷ የተወለደው ልጅ ሰነፍና ሞኝ ቢሆን ከሌላዋ የተወለደው ብልህና ብርቱ ሆኖ በዙፋን ነጋሢ ሆኖ በመከተል ስም እንዲያስጠራ ነው ።

በዚህ ምክንያት እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመን የነበሩት ነገሥታት ከአማራ ወይም ከትግሬ አንዲት ሴት በደንብ ግራ ባልተሐት አሰኝተው ካገቡ በኋላ በዚያው ሰሞን ከሐድያ ወይም ከደዋሮ ገራዶች ሴት ልጅ አንዷን አስመጥተው አብዛኛውን ጊዜ በእሌኒ ስም ክርስትና አስነሥተው ሲያገቡ ኖረዋል ። ከዚህ አልፈው ደግሞ ሌሎቹን እንዲወልዱላቸው በዕቁባት ስም ያስቀምጧቸዋል ። ራሳቸው ያፄ ልብነ ድንግል አባት ዓፄ ናዖድ ፭ ሚስቶች እንደነበሩዋቸው አልቫሬዝ በመጽሐፉ ያረጋግጣል (2) ።

አፄ ልብነ ድንግል በዘመነ መንግሥታቸው መጀመሪያ ላይ ያኸን ከአያት ከቅድም አያት የመጣ ልማድ ለመፈጸም የተገደዱ ይመስላል ። በቅርብ የተዋወቋቸው እንአልቫሬዝ በመጽሐፋቸው ላይ እንደዚህ ብለው ጽፈዋል ''ነገሥታቱ በዙሪያቸው ካሉት ከእስላሞቹ ነገሥታት ፭ ወይም ፮ ልጆቻቸውን አግብተዋል ። ከአሕዛቦቹ ጋር ግን አይጋቡም (3) ። ነገር ግን ከዶባ ፪ ወይም ፫ ፣ ከደንከል አንዲት ፣ ከአዳል አንዲት ፤ ከሐድያ አንዲት ያገቡ ነበር ።

(1) Les chroniques de Zara Yaeqob et de Beide Mariam-Jules perruchon ገጽ 38 . 149

(2) አልቫሬዝ . . . . . በነአቶ ግርማ ትርጉም ገጽ 299

(3) አሕዛቦች የሚለው ሃይማኖት የሌላቸውን ነው

ቄስ ዮሐንስ (አፄ ልብነ ድንግል) ከሐድያ አንዲት ልጅ ሊያገቡ ተስፋ ሰጥ ተው ሳለ በኋላ ጥርሷ ረገዥዥም (ገጣጣ) ስለሆነ . . . እምቢ ብለው ላንድ ትልቅ ቢትወደድ ክርስትና አስነሥተው ዳሯት ። ከዚያ ወዲህ እንዲህ የመሰለውን ጋብቻ ጠልተው አንዲት የክርስቲያን ልጅ አገቡና ለወደፊቱ በወንጌል ሕግ ብቻ (ባን ዲት ሴት ተወስኜ) እኖራለሁ አሉ (1) ።»

ሐድያ ወደፊት ባሉት ምዕራፎች ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን ። በጂምግ ራፊው ላይ እንደሚታየው በጉራጌ ፣ በአሩሲ ፣ በጃንጀሮ መካከል አሁን በከምባታ አውራጃ ግዛት ውስጥ የሚገኝ በዚያን ጊዜ ታላቅ አውራጃ ባላባቱ ገራድ በሚባል የማዕርግ ስም የሚጠራ የተከበረ የእስላም ባላባት ነው ። ከዶባ ሁለት ወይም ሦስት ያገባሉ የሚለው ይህ ዶባ በሸዋ በመንዝና በመራቤቴ መካከል የሚገኘው አይደለም ። ነገር ግን ዛሬ በዋጅራትና በራያ ያለውን ወይም ራሱን ራያን ነው ። ይህ አገር በዚህ ሥፍራ በዚህ ስም እስከ ዛሬ መኖሩን ወይም በነአፄ በዕደ ማርያም ዘመን ዶብእ ወይም ዶባ ይባል የነበረው ከጋላ ወረራ ወዲህ በዋጅራትና በራያ ስያሜ መለወጡን በትክክል አላረጋገጥም ።

እነዚህ የዶባ ሰዎች ባፄ በዕደ ማርያምና ባፄ እስክንድር ዘመን እየሸፈቱ ያለ ችግሩትን በኋላም የዣን አሞራና የዣን ቀንጠፋ ወታደሮች ወግተው ያሸነፏቸውን በጠቅላላው ግዕዙ "ሰብአ ዶባ" ይላቸዋል (2) ። የኢትዮጵያ ነገሥታት ከነዚህ ባላ ባት ተወላጆች ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት ዕቁብ[illegible]ገቡ የነበረው የዘወትር ሽፍት
ነታቸውን በጋብቻ ገመድ አሥሮ በታማኝነት እንዲኖሩ ለማድረግ ይሆናል ።

አፄ ልብነ ድንግል ግን በዘመናቸው ይህ በብዛት ሴት ማግባት ወይም ማስቀ መጥ ከክርስትና ሃይማኖትና ከወንጌል ትእዛዝ ውጪ መሆኑን በመረዳት (3) ይኸ ንን የመሰለው ሥራ የእስላሞች ወይም ሃይማኖት የሌላቸው የአረመኔዎች ነው በማለት እርሳቸው ግን ባንዲት ሴት ለመወሰን ቁርጥ አሳብ አድርገው እቴጌ ሰብለ ወንጌልን ብቻ አገቡ ።

ይኸንንም ውሳኔያቸውን ያገራችን ታሪክ ነገሥት እነአልቫሬጽ የጻፉትን በማ ጽደቅ እንደዚህ ሲል መዝግቦት ይገኛል ። «በነገሠ ጊዜ እርምጃውን በቤተ ክርስ ቲያን ሕግ አደረገ እርሷ ከወሰነችለት አልተላለፈም ። ከርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥ ታት ተለይቶ የሚመሰገን ነገር በማድረጉ የሚያሳማ ነገር ባለመፈጸሙ የእግዚአ ብሔር ጸጋ በላዩ ላይ ወረደ ። ይኸም ጸጋ እንደ ቤተ ክርስቲያን ደንብ አንድ ባል ለአንዲት ሴት መሆንን የተቀደሰ የጋብቻን ፍቅር አሳደረበት ። ራሷን ለባሏ በማስ ገዛት የምታሳምር መልካም ሴት አጋቡት ። ንጉሡም የመልኳን ውበት ዓይቶ ወደ

(1) . . . . . ዣን ቴምፖራል ገጽ 76 ምዕ. 118
Verdadeira informacao F. Alvarez 118

(2) Les Chroniques de Zara ...... 138, 142-145

(3) ማቴ. ምዕ. 5 ቍ. 31 - 32 ። ምዕ 19 ቍ. 3 - 11

ዳት ። ይቺም ሴት ንግሥት ሰብለ ወንጌል ትባላለች ብዙ ልጆችም ወለደች ። (1) ።

ታሪክ ነገሥቱ ያገቡት በንጉሡ ጊዜ መሆኑን ያመለክታል ። ነገር ግን የነገሡት በሺ፭፻፸፪ ዓ. ም. በአሥራ አንድ ዓመታቸው ፤ ሥልጣን የጨበጡት በ፲፭፻፹፰ ዓ. ም. ግድም በ፲፱ ዓመታቸው ስለሆን ምናልባት ያገቡት በመጀመሪያው በንግሣቸው ጊዜ ሳይሆን ሥልጣን በጨበጡበት በአሥራ ዘጠኝ ዓመት ያም ቢቀር ከዚያ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ በአሥራ ስድስትና በአሥራ ሰባት ዓመታቸው ላይ ይሆናል ።

ከርሳቸውም ብዙ ልጆች ወለዱ የሚለው ወንድ ልጆች ፊቅጦርን ፤ ያዕቆብን ፤ ገላውዴዎስን ፤ ሚናስን ፤ ሴት ልጆች ታዎድራን ወለተ ቅዱሳንን ሰበነ ጊዮርጊስን አመተ ጊዮርጊስን ነው ። ስለዚህ አፄ ልብነ ድንግል ቀድሞ አባቶቻቸው የቀኝ ባለ ቤት የግራ ባለቤት እያሉ ሁለትም ከሁለትም በላይ እያገቡ በየሥፍራው ከየባላባቶቹ እያስመጡ በዕቁባትነት ያስቀምጡ የነበረውን ሽረው የክርስትና ሃይማኖት እንደሚያዘው ባንዲት ሴት በሰብለ ወንጌል ተወስነው የደስታቸውንም የመከራቸውንም ጊዜ ከዚህ ሴት ጋር አሳለፉ ።

ወደፊት የጦርነቱን ታሪክ በየምዕራፉ ስናነብ ከነዚሁ ከተወለዱት ልጆች ውስጥ ፊቅጦር በውጊያ ላይ መሞቱን ሚናስ ተማርኮ ወደ ዘቢድ ባሻ አረብያ መላኩንና በኋላ በግራኝ ልጅ ተለውጦ መመለሱን ገላውዴዎስ ባባታቸው እግር ተተክተው የፖርቱጋልን ርዳታ ISIG ግራኝን በማስገደል ያባታቸውን ደም መበቀላቸውን የያዕቆብን ብዙ ዘመን ኖሮ መሞት እናገኛለን ። ይኸን ሁኔታ ቀደም አድርጎ ራጉኤል መልአኩ ላፄ ልብነ ድንግል "ፊ. ይመውት (ፊቅጦር ይሞታል) ፡ ገ. ይነግሥ (ገላውዴዎስ ይነግሣል) ፡ ሚ. ይሠየጥ (ሚናስ ይሸጣል) ፡ ያ. ይነብር (ያዕቆብ ይኖራል)" ብሎ በሕልም (በራእይ) ነግሮአቸው እንደነበር በገድለ ራጉኤል ተጽፎአል (2) ።

የእቴጌ ሰብለ ወንጌልን አገር አንዳንድ መጽሐፍ ከሰሜን ባንድ ወገን ከትግሬም ተወላጅ የሚያደርጋቸው አለ ። ነገር ግን የነገሥታቱ ዝርዝር የሕይወታቸው ታሪክ እንደማይገኝ ሁሉ ከዚያ የባሰ የሚስቶቻቸው የእቴጌዎች የሕይወታቸው ታሪክ ባጭሩም ቢሆን ማግኘት በጣም ብርቅ ነው ። ስለዚህ የእቴጌ ሰብለ ወንጌል ከትግሬና ከሰሜን መወለዳቸውን በኔ በኩል ማሳመንም ማስተባበልም አልችልም ። የኝህ ሴት ዋናው አገራቸው በጐጃም መሆኑን ለማረጋገጥ ፤ የዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዜና መዋዕል እንደዚህ ብሏል «በደብረ ወርቅ ፊት ለፊት በግማ መንግሥተ

(1) ወሰበ ነግሠ ረሰየ ሁረቶ ቤተ ክርስቲያናዊተ .... ወእምድኅረ ቀደምትኒ ነገሥት ከነ ይገብር ዘተወደሰ ወኢየአዱ እምውሳኔ ዘወሰነት ሎቱ .... መርዓዊ ፩ዱ ለአሐቲ፡ መርዓት በአምጣነ ቀኖናሃ ለቤተ ክርስቲያን ..... ወአእተወ ሎቱ ብእሲተ ሠናይተ ዘታሠረት ርዕሳ በቅኔ ..... እስመ ፈተወ ንጉሥ ስነ ዘኢሃ ፤ ወስመ ዛእቲ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ፤ ወወለደ እምኔሃ ደቂቀ ወአዋልደ ..... ። ታሪከ ነገሥት ገጽ ፺፮

(2) ገድለ ራጉኤል ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕራፍ ፱ ገጽ 32 - 33

በእኍቲሁ፡ አብ፡ ወወልዱ፡ ወ
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እኁለ ትሥሉስ፡ እ
ሐዱ ናግ፡ ሰገድ፡ ንጉሥ፡ እንዘ፡
ሀለው፡ ኩ፡ በጐንደ፡ ሐመ፡ ወሀ
ልኩ፡ በጺማ፡ በሀሉ፡ ፋሲል፡፡ ምድ
ረ ሀቢባር፡ ወምድረ፡ እናርያ ጋ፡፡
ወመድረ፡ እናርያ፡፡ አሉ ንተ፡ ፫
ምድረ፡ ለዓመተ፡ ጊዮርጊስ፡ ወ
ለወልተ፡ ቍልዩሳን፡ መንፈቀ፡ እ
ሉ፡ [illegible] ወመንፈቁ፡ ለሠር
ፀ፡ ማርያም፡ እስመ፡ ርስተ፡ ዚአ
ሆሙ እቶ፡ ምክሉ፡ ጃንሆይ መሉ
ለወግዘት፡ ከመ፡ ኢይግፍዕዎ፡
ወኢይግፍዖሙ፡ ኢይሂድዎ፡ ኢይ
ሂዱሙ፡ መንፈቀ፡ ሀቢባር፡ ወመን
ፈቁ፡ እናርያ ጋ፡ ወመንፈቀ፡ እናር
ያ፡ መንፈቁ፡ ለሠርፀ፡ ማርያም፡ ወ
መንፈቁ፡ ለ፳ ወ፬ ካህናት፡ ወምድረ፡
በውኗሂ፡ ወሀ ክሎ፡ ለንግሥት፡ ስ
ብለ ወንጌል፡ ከመ፡ ይ ከ፡ ና፡ ለ ይረባ፡
ወእእ፡ ለንቡር፡ ቤቱ፡ እንዘ ሀ ቀቢ
ሠሀት፡ ንጉሠ ኢየሱስ፡፡ ወምግሬ፡ ብ
ሐት ወደድ፡ ሠርፀ ማርያም፡ ወቀኝ
ብሕተ ወደድ፡ በድሉ፡ አዝማቾ፡ በ
ግራ፡ ቀኛዝ፡ ደጋኝ፡ ይስሐቅ፡ ግራ
ቀኛዝ፡ ኣዴ፡ ግራስ፡ ዕንቆ፡ ፋ፡ ኦኤል፡፡
ግራ ጌታ፡ ተስፋ፡ ኢየሱስ፡ ወቀኝ
እጌታ፡ ወሰንጌ፡፡ ሊቀ መኳስ፡ ግር
ማቸ፡ ወጎዴግ፡ ጊዮርጊስ፡ ቃቂ
ቃቸ፡ ብሉሉ፡ ፀራጅ፡ ማስሬ፡ ዓስ
ሬት፡ ወቂስ፡ ሐጼ፡ ቴዎግሎስ፡ ሀ
ቃቤ፡ ሠዐት፡ ዘደብረ ምሥጢር፡
ብትሩ፡ ወቂስ፡ ገብዝ፡ ወልደ፡ ጊዮርጊስ፡
ቤት፡ ጠባቂ፡ ጌታ፡ ሂሳይ፡ [illegible] ጕዝ
ም፡ ንጉሽ፡ ሠርፀ፡ ማርያም፡ ዘንቱ፡
ጉልት፡ ወዘንቱ፡ ሠርፀ ተክዘ [illegible]

ወዘተ ፷ ግሉ፡ እስከ፡ ወለደ፡ ው
ሉደ፡ ሙ፡ እመ ሂ፡ ንጉሥ፡ ወእመ
ሂ፡ ጳጳስ፡ ወእመ ሂ፡ መኰንን፡ ው
ጉዛን፡ ላይ ኩሉ፡ በሥልጣኑ፡ ወወ
ልዱ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወእሮ
እግዝእትነ፡ ማርያም፡ በሥልጣ
ጥሮስ፡ ወጳውሎስ፡ ብእሲሆ
ሎሙ፡ ቅዱሳን፡ [illegible]
መንፈስቅዱስ፡ ለዓለመ፡ ዓለም
አሜን፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል የፋሲ
ካን በዓል በጕጃም በተለይ በዲማ በዋለበት ቀን
ለቤት ልጆቻቸው ለዓመተ ጊዮርጊስና ለወለተ ቅዱ
ሳን የሀቢባርንና የእናውጋን የእናርያን አጋማሹን
ለሠርፀ ማርያም (ጕጃም ንጋሽ ?) የባውግ (?)ን ለባለ
ቤታቸው ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል በጉልትነት ሲሰ
ጡ እንደአማኝ የቆጠሩዋቸው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ
ኢየሱስ ዓባይ ዳር አብሳማኑር ንጉሡ መስለሙት ማ
ርኮ የገደለው ፤ በዚህ ቀን ልጁ ብዕሴ እግዚአብሔርና
ቀኝ ጌታ ወሰንጌ አብረው ሞተዋል ። ቢቶደድ ሠርጸ
በእምባ ገሹን ጦርነት መሪውን አህሙድን ማርኮ
ለንጉሡ ያቀረበ ፤ ቀኙ ቢቶደድ በድሌ (በድል ሰገድ
ለንጉሡ ያቀረበ ፤ ቀኙ ቢቶደድ በድሌ (በድል ሰገድ
ወይስ በእድሉ ወይም በድላይ ?) በአይፋርስ ጦርነት
የሞተ [illegible] ፣ ከአዛዦቹ መካከል የግራው አዛዥ
ደጋኝ የሚለው ራስ ደገልሃንን ነው ምናልባት ይህ
ጉልት የተሰጠው ከግራኝ ጦርነት ቀደም ብሎ ባለው
ጊዜ ውስጥ እማች ሆኖ ይረዳው ከፍ ከማለቱ በፊት
ይሆናል ስሙ ደጋልሃን ደገልሃን - ደጋኝ ደገል እያ
ለ ይለዋወጣል ። በአይፋርስ ጦርነት ከተከለ ኢየሱስ
ጋር ይስሐቅ የቢገምድር ገዥ በአሊማጅራህ እጅ የተ
ገደለው ተስፋ ኢየሱስ የባሕር ዓምበ (ሰማን ውስጥ
ገዥ የነበረው ግርማ ዝግ)(የራሱ ወሰን ሰገድ ወንድ
ም ?) ጎዴግ ጊዮርጊስ የሚለው በተጉለት ሲዋጋ በ
ምርኮኝነት የሞተው ይሁን አይታወቅም ሌሎቹ
በዚህ ዘመን አሉ ። ጽራግ ማሠሬ አሥራት (ወደ
ኢየሩሳሌም ተልኮ የነበረውና የባሌው ናስር ገ
ራድ የገደለው ይሆን ?)

ሰማያትን ያሳነፀችውን አገሯ ጕጃም የሆነውን ስሟ ሰብለ ወንጌል የምትባለውን አቡቱ አጋባው» (1) ።

ይኸኛው ዜና መዋዕል አባትዬው ዓፄ ናዖድ እንዳጋቡዋቸው ያወሳል ። አባትዬው ዓፄ ናዖድ የሞቱት በ፲፭፻፪ ዓ. ም. ስለሆነ ከአሥራ አንድ ዓመታቸው በፊት አጋቡዋቸው ማለት ሳይቸግር አይቀርም ። ምናልባት አባትዬው በሕይወት ሳሉ እጮተውላቸው አብረው ቆይተው በኋላ ተጋብተው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ ከ፲፭፻፲፱ ዓ.ም. ጀምሮ ባላቸው እስኪሞቱ ድረስ መከራውንና ስደቱን ተሸክመው ኖረው ባላቸው በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. በመስከረም አምስት ቀን ካረፉ ወዲህ ልጆቻቸውን ይዘው በደብረ ዳሞ በጸሎትና በኀዘን ሲኖሩ በመካከሉ የፖርቱጋሎች ርዳታ በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. በደረሰ ጊዜ ተቀብለው በማስተናገድ ግራኝ እስመድ በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ሲሞት ዓይተው ከዚያም ከልጆቻቸው ከገላውዴዎስና ከሚናስ ጋር ገዝተው እስከ ልጅ ልጃቸው እስከ አፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን ደርሰው አርፈዋል (2) ።

የሞቱበት ዘመን አፄ ሠርፀ ድንግል በነገሡ በአምስተኛው ዓመት መሆኑን ዜና መዋዕሉ ስለሚያረጋግጥ አፄ ሠርፀ ድንግል የነገሡት በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ስለሆነ ንግሥት ሰብለ ወንጌል የሞቱት በ፲፭፻፷፮ ዓ. ም. መሆኑ ነው ። ምናልባት ከዔ ልብነ ድንግል ጋር በ፲፭፻፪ ዓ. ም. ግድም ሲጋቡ ዕድሜያቸው እንደ ባለቤታቸው አሥራ አንድ ዓመት ግድም እንደሆነ ሲሞቱ ጠቅላላ ዕድሜያቸው ወደ ሰባ ዓመት ደርሶ ነበር ማለት ነው ። የሠርፀ ድንግልን ዜና መዋዕል የጻፈው ወልደ ሃይማኖት "ወበሳኒታሁ ዘውእቱ ዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን . . . . . ወውእቱ ዕለት እመ ፳ ወ፫ ለወርኀ ኅዳር . . . . . ወቦቱ ኮነ ዕለተ ዕረፍታ ለንግሥት ሰብለ ወንጌል መፍቀሪተ ጾም ወጸሎት ፈራሂተ እግዚአብሔር . . . . ." ስለሚል ወሩ ኅዳር ቀኑ ፳፫ ዕለቱ እሑድ መሆኑን ያስረዳል ።

የኚህ ንግሥት በፖለቲካ ፥ በሃይማኖት ፥ በአስተዳደር ገብተው የሠሩበት ዝርዝር ታሪኩ ከባላቸው ሞት በኋላ በልጆቻቸው በንጉሥ ገላውዴዎስ ዘመን ላይ ወደ ፊት ይነበባል ።

ከአፄ ልብነ ድንግል በፊት የነበሩት ነገሥታት ዘር ለማፍራት ሲሉ ብዙ ሴቶች ያገቡ ዕቁባትም ያስቀምጡ እንደነበረ ተረድተናል ። አፄ ልብነ ድንግል ግን በኚሁ በእቴጌ ሰብለ ወንጌል ብቻ ተወስነው ሲኖሩ እላይ እንደተመለከትነው አራት ወንዶች አራት ሴቶች ልጆች ስለወለዱ መጽሐፍ በሲና ምድረ በዳ መና ለእስራኤሎች ወርዶ በመልቀም የተሻሙትን ከተረከበት ላይ ብዙም የለቀሙ አልተረፉቸውም ጥቂትም የለቀሙ አልጐደላቸውም እንዳለው ልብነ ድንግልም ዘር በማ

(1) «ወአስተዋሰቦ አቡሁ ብእሲተ እምሀገረ ጐጃም ዘስማ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ዘሐነፀቶ ለመንግሥተ ሰማያት በግማ ዘእንጻረ ደብረ ወርቅ» ታሪክ ዘገንቦ ነገሥት አድያም ሰገድ መንግሥት ብርሃን ሞገሳ ትዖዲ ያሳተመው ገጽ 7

(2) ያፄ ሠርፀ ድንግል (መለክ ሰገድ) ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ ፴ ።

ትረፍ ረገድ ብዙ ካገቡት አልጐደላቸውም ። እንዲያውም የሸዋ መሣፍንት እነ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፣ የጐንደር ነገሥታት ፣ እነ ዓፄ ፋሲል ፣ የጐጃም መሣፍንት እነ ታላቅ ራስ ኃይሉ ሁሉም ያዔ ልብነ ድንግል ዘሮች ስለሆኑ የርሳቸውን ባንዲት ሚስት መወሰን እግዚአብሔር እንደባረከው ያስረዳል (1) ።

## ምዕራፍ ፲፬

## ኢትዮጵያ - ኢየሩሳሌም - ግብፅ - የኢትዮጵያ መላክተኞች በካይሮ ፲፱፻፬ ዓ. ም.

በግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ ፳፪ የንግሥት ሕንደኬ ሹም ከሹማምንቶቿ ሁሉ የበለጠ በከብቷ ሁሉ የሠለጠነ ገርንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ለስግደት ወርዶ በፊልጶስ መጠመቁ ተጽፏል ። በተለይ ግን ኢትዮጵያ ክርስትናን ከተቀበለችበት ከአራተኛው መቶ ዓ. ም. ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ስለት ለማድረግ ለመሳለምና ለመመለስ ወይም እዚያው እተቀደሰው አገር ኖሮ ለመሞት ሁልጊዜ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ተመላላሽ አለ ።

ቅዱስ ዠሮም የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስን በመጀመሪያ ከዕብራይስጥ ወደ ሮማይስጥ የተረጐመው ኢየሩሳሌምን በአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት (፫፻፺፮ ፬፻፲፮ ዓ. ም.) ሊሳለም ሄዶ ሳለ ለወገኖቹ ደብዳቤ ሲጽፍ በኢየሩሳሌም በአርመኖች ፣ በሕንዶች ፣ በፋርሶች ክርስቲያኖች መካከል ኢትዮጵያውያንም መኖራቸውን ገልጿል (2) ።

በ፫ኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ የፈረንጆቹን ክርስቲያኖች ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን የወሰደው ሳላሀ ዲን (ሰላጢን) የሚባለው የዓረቦች ንጉሠ ነገሥት ፲፩፻፹፯ - ፲፪፻ ፳፰) በኢትዮጵያ ንጉሥ ዓፄ ላሊበላ በነበረበት ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ማኅበር እቅዱስ መቃብር አጠገብ ሁለት ክፍል ቤት እንደዚሁም መስቀል እተገኘበት ቦታ አንድ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰጣቸው ያዘዘበት ማስረጃ አለ (3)። የዚህ የሡልጣን ሳላሀ ዲን ማስረጃ የቀድሞውን ይዞታ ለማጽደቅ ነው እንጂ ከርሱ በፊት ለኢትዮጵያውያን ቤትም ቤተ ክርስቲያንም በዚያው በቅዱስ ቦታ እንደነበራቸው የታወቀ ነው ። አሁንም ያሉበት ያው ነው ።


ከዚያ ወዲህ ደግሞ በቅርቡ በዓፄ ዮሐንስ ጊዜ አሁን የእሥራኤል ግዛትና ክፍል ወደ ሆነው ኢየሩሳሌም የገዳሙ መምህር የነበሩት መምህር ወልደ ሰማዕት ሰፊ ቦታ ገዝተው የኪዳነ ምሕረት ገዳም ባዔ ዮሐንስ ስም ሥራው ተጀምሮ ሳይፈጸም ዓፄ ዮሐንስ ስለሞቱ ዓፄ ምኒልክ ፩ሺ ወቄት ወርቅ ልከው አስጨረሱት ። ለገዳሙም መተዳደሪያ ርሳቸውና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ መኳንንቶቻቸው ራስ

(1) ዘፀዓት ምዕ. 16 - 18

(2) Etiopi in Palestina የሚባለው የሀንሪኮ ቼሩሊ ፩ኛ ቮሊዩም ገጽ 1 - 2

(3) Etiopi in palestina ,, ,, ፩ኛ ቮሊዩም ገጽ 31 - 32

ISIC



ዐፄ ዓምደ ጽዮን በኢየሩሳሌም ገዳም ለምትገኘው ለማርያም መጽሐፈ ነገሥት የሰጡበት ጽሑፍ በሮማ የቫቲካን ቤተ መጻሕፍት በቁጥር ፳፭ ተቀምጦ የሚገኝ።

ወልዴ ፣ አፈ ንጉሥ ነሲቡ ፡ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፣ ወይዘሮ አልታየ ፣ ደጃች ባልቻ በግል ሀብታቸው ዙሪያውን ያሠሩት ልዩ ልዩ ሕንፃ እስከዛሬ የምእመናኑ የኑሮ መጠገኛ ሆኖ ይኖራል ። ከርሱም ራቅ ብሎ ዋናው ቆንስላችን ያለበት ንግሥት ዘውዲቱ ያሠሩት ታላቅ ሕንፃ አብሮ አለ ።

የሆነ ሆኖ የቅርቡን እንተውና ወደኋላ ተመልሰን የኢየሩሳሌምንና የኢትዮጵያን በ፲፪ና በ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. የነበረውን ግንኙነት እንመልከት ።

በዚሁ በቅዱሱ ቦታ ነዋሪ የኢትዮጵያ ማኅበርና ገዳም ከመኖሩ የተነሣ ይልቁንም የጌታችንን መቃብር ለመሳለም እላይ እንዳመለከትነው በያመቱ የሚሄደው ብዙ ነው ። ነገሥታቱም ራሳቸው ከአገራቸው መውጣት ስለማይሆንላቸው ሹማቸውን ስለት እያስያዙ ለኢየሩሳሌም መጻሕፍት አልባሳት ንዋየ ቅድሳት በየጊዜው መላካቸው በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል ።

ዳሩ ግን ከአፄ ልብነ ድንግል ወዲህ በግራኝ ወረራ ምክንያት እስከ አፄ ቴዎድሮስ መነሣት ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንድ ወገን ስለተዳከመ ፡ ባገር ላይም መከፋፈል ወይም የውስጥ ጦርነት ጊዜ አልሰጥ በማለቱ ነገሥታቱ ጊዜና ችሎታ አግኝተው በኢየሩሳሌም ላሉት ምእመናን በየጊዜው ገንዘብ እየላኩ ሊያግ ፏቸው አልቻሉም ። ስለዚህ ከይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ድረስ በሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለኢየሩሳሌም ገዳማትን የላኩዋቸው ዕቃዎችና በተለይ መጻሕፍቱ በሚያሳዝን አኳኋን በየጊዜው እየተሸጡ ወይም እንደመታያ እየተሰጡ አብዛኞቹ አልቀዋል ።

ለምሳሌ ዓፄ ዓምደ ጽዮን (፲፫፻፲፮ - ፲፫፻፵፬) በዘመኑ አጽፎ ወደ ኢየሩሳሌም የላከው መጽሐፈ ነገሥት ሮማ በቫቲካኑ መጻሕፍት ቤት በቍጥር ፫ ተመድቦ ይኖራል ። ይህ መጽሐፍ ለኢየሩሳሌም መላኩን ለማስረዳት በመጨረሻው ገጽ ላይ "ዘንተ መጽሐፈ ነገሥት በዓዕኑ አነ ዓምደ ጽዮን ንጉሥ ወስመ መንግሥትየ ገብረ መስቀል ንጉሠ ኢትዮጵያ ለእግዝእትየ ማርያም ለኢየሩሳሌም ከመ ታስተስሪ ሊተ ኃበ ፍቁር ወልዳ እመ ይመጽእ በስብሐቲሁ ከመ ይረሲ ማኅደርየ ምስለ ቅዱሳኒሁ ወኅሩያኒሁ ለዓለመ ዓለም አሜን" ይልና ቀጥሎ ደግሞ ደበስበስ ባለ አጻጻፍ "አ አበውየ ወአኃውየ (1) ። እለ አንበብክምዋ ለዛቲ መጽሐፍ ዘክሩኒ በጸሎትክሙ ከመ ይምሐረኒ ወይሣሀለኒ . . . . . ." የሚል አለበት ።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ለኢየሩሳሌም ገዳም በየጊዜው የላኩትን ሁሉ ከነማስረጃው ሰብስበው በሁለት ሾሊም በኢጣሊያ ቋንቋ ያሳተሙት ሀንሪኮ ቼሩሊ በዚሁ በርሳቸው መጽሐፍ ላይ ፡

፩. ያግብአ ጽዮን ስመ መንግሥቱ ሰሎሞን (፲፪፻፸፯ - ፲፪፻፹፮) በኢየሩሳሌም ላሉት ለኢትዮጵያ መነኮሳት በጻፈው ደብዳቤ ላይ የሐር ቀይ መጐናጸፊያ መቶ ጫፍ የወገቡን ንጉሣዊ ስቅ በበዓልና በቅዳሴ ብቻ እንዲጠቀሙበት ልኮ በጸ

(1) የሚለው ግን አአበዊየ ወአኃዊየ ነው ስሕተት ወይም የዘመኑ የሰዋስው መንገድ እንደሆነ አይታወቅም ። በኔ በኩል የዘመኑ የግዕዝ አካሄድ ይመስለኛል ።

ISIC

በስመ፡አብ፡ወወል
ድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ፡፡
በኵሉ፡ልብየ፡ዘኪያ
ሁ፡ሰመልክ፡፡በኵሉ፡
ኃይልየ፡ወበኵሉ፡ነ
ፍስየ፡ወበኵሉ፡ሕሊ
ናየ፡ዘግቱ፡አስምክ
ዘእኅዝ፡በሕብለ፡አ
ምልኮቱ፡ዘኢይትበ
ተክ፡ዘቦቱ፡አሐዱ፡
ለዝሉፉ፡ወኢ[illegible]ቅ
ወከ
ተጽሕፈት፡ዛቲ፡መል
እክት፡ውስተ፡ዛቲ፡መ
ጽሐፈ፡ሴኖዶስ፡እም
ኀቤየ፡እምኀበ፡ዘርአ
ያዕቆብ፡ወልደ፡መን
ግሥትየ፡ቴሸጠንሀ
ፕሀ፡እምአመ፡አንበ
ረኒ፡አምላክ፡እስራ
ኤል፡በብዝኃ፡ምሕረ
ቱ፡ዲበ፡መንበረ፡መ

ንግሥተ፡ኢትዮጵያ፡
በ፲ወ፩ዓመት፡እንዘ፡ሀሎ
ኩ፡ውስተ፡ሀገረ፡ሰ.ሾ፡
እንተ፡ትሰመይ፡ተጉለ
ት፡፡ት፡በሰላም፡ኀበ፡ፍ
ቁራንየ፡ማኅበረ፡ቅዱ
ሳን፡እለ፡ይነብሩ፡ወ
ስተ፡ኢየሩሳሌም፡ሀገ
ር፡ቅድስት፡በሰላመ፡እ
ግዚአብሔር፡አሚንቶ
እስተበፅዓክሙ፡ፈድ
ፋደ፡ተሰምዐ፡አንክሙ፡
ቂውሞን፡በታለ፡ወንገ
ል፡ዘይቤ፡ዘኢኀደገ፡
ሰባሁ፡ወእሞ፡ወብእ
ሲቶ፡ወውሉዶ፡ወገራ
ውሂሁ፡ወኵሉ፡ዘቦ
ወበእንተዝ፡ኀደግሙ፡
ዓለመ፡ወሀለክሙ፡
ውስተ፡ኦርሆተ፡ም
ንኵስና፡ወዳግመ፡
ሂወወክሙ፡ታስ፡ነቢ
ይ፡ዘይቤ፡ኢይበውእ፡

ከዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታሪካዊ ደብዳቤ የመጀመሪያው ገጽ ።

ሎታችሁም እንድታስቡኝ ብኋል (1) ።

፪. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ገዳም ለሚቀመጡት ለኢትዮጵያውያን መነኮሳት እንድ በብራና በጥሩ የተጻፈ የሲኖዶስ መጽሐፍ ሲልኩ የመግ መሪያ ዎቹ አራት ገጾች የርሳቸው ሽኚ ደብዳቤዎች ናቸው ። በደብዳቤው ላይ ኢየሩሳሌ ምን ለረገጠው እግራቸው ፡ ለዳሰሰው እጃቸው ፡ ለተመለከተው ዓይናቸው በግጥም መልክ ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ለመነኮሳቱ መተዳደሪያ በምድረ ዝበላ ወይም ዝበል ! ከ፪ ዓመት ግብር የሚወጣውን ፩፪ ወቄት ወርቅ ሰጥተዋል (2) ።

ይኸ ሁሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለኢየሩሳሌም በየጊዜው የላኩት ንዋየ ቅድ ሳትና መጻሕፍት በገዳማችን ቢገኝ ኖሮ በዛሬ ጊዜ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ከፍ ያለ በብዙ ሚሊዮን ብር የማይገኝ የታሪክ ቅርስ ሊኖረው በቻለ ። ነገር ግን የገዳሙ ኃላፊና ምእመናኑ ከዚህ በፊት እንዳልነው በየጊዜው እየቸገራቸውም ሳይቸግራቸውም በሺያጭም በስጦታም አባክነውት አብዛኛው በተለይ መጻሕ ፍቱ (BIBLEOTECA VATICANA) ከሚባል ሮማ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ መጻሕፍት ቤት ይገኛል ፡ ዓፄ ዓምደ ጽዮንና ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የላኳቸው ሁለቱንም መጻሕ ፍት ከኛ ገዳም ወጥተው እዚያ የተቀመጡትን በጸጸት ዓይን ተመልክቻለሁ ።

የሆነ ሆኖ ይኸ ሁሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት ስለ ኢየሩሳሌም ያላቸውን ፍቅር ያሳየናል ። ይኸንንም ፍቅር ያሳደረው የዳዊት ከተማ ጌታችን ተሰቅሎ የተቀበረ ባት በመሆኗ ነገሥታቱ ከዳዊት ተወልደናል ብለው ከማመናቸው ጋር ፍጹም ክር ስቲያኖች በመሆናቸው ነው ። ይቺም ቅድስት ቦታ ከክርስቲያን መንግሥት ከቁስ ጥንጥንያ እጅ ወጥታ መገ መሪያ በዓረቦች ከዚያ በግብፆች በመጨረሻ በቱርኮች በመገዛቷ ያላቸው ጸጸት ከፍ ያለ ሆኖ የጸጸቱ ቅርስ እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ (፲፰፻፵፰ - ፲፰፻፷) ደርሶ የቱርክን የዚህን ዘመን ኃይል ሳይገምቱ አስለቅቃለሁ የሚል ምኞት ነበራቸው ።

ካፄ ቴዎድሮስ በፊት በጐንደርም በሸዋም የነበሩት ነገሥታት ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች ግዛት ነፃ ለማውጣት የጋለ ምኞት ነበራቸው ። ምኞታቸውም ራሳቸው በዚህ በአሥራ አራተኛውና በአሥራ አምስተኛው ፡ በአሥራ ስድስተኛው ዘመን የመርከብ ኃይል እንደሌላቸው ስለሚያውቁ ኃይላቸውን የመርከብ ኃይል ካላቸው ከአውሮፓ ክርስቲያኖች ጋር በማስተባበር ነበር ። የዚህን ስሜት አራተኛው ሔንሪ የሚባለው የእንግሊዝ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ሊሳለም በሄደበት በ፲፫፻፺፪ ዓ. ም. እዚያ ካሉት ከኢትዮጵያውያኑ ምእመናን ሰምቶ ስለዚሁ ጉዳይ መተባበሩን ለመግለጽ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ በ፲፬፻ ዓ. ም. ደብዳቤ ጽፎ አባ ዮሐንስ በሚባሉ ጳጳስ እጅ ልኳል (3) ።

(1) Etiopi in palestina ፩ኛ ቮሊም ምዕ. 11 ገጽ 89 - 90
(2) የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 38
(3) Etiopi in Palestina ፩ኛ ቮሊዩም ገጽ 201 - 204

በይብጻበው ላይ ይብጻበው የተላከለትን የኢትዮጵያን ንጉሥ ስሙን አይጠቅስም ። ነገር ግን ከ፲፫፻፲፱ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፲፩፻፲ ዓ. ም. ድረስ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው ከኢየሩሳሌም ግማደ መስቀል የመጣለት ያዒ ዘርዓ ያዕቆብ አባት ዓፄ ዳዊት ነው ። ዳሩ ግን ኢየሩሳሌምን የማስለቀቁ ነገር ከ፲፻ ፺፩ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ፲፪፻ ፺፩ ዓ. ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የአውሮፓ ነገሥታት ተባብረው ፰ ጊዜ በውጊያ ፈትነው ሳይሳካ የቀረው ኢትዮጵያ በምንም ዓይነት ብትጨምር ዋጋ እንደሌለው የታወቀ ነው ። ስለዚህ መደምደሚያውን የኢየሩሳሌም ግዛት ከግብፆቹና ከዓረቦቹ ቀጥሎም ከቱርኮች እጅ ሊወጣ አልቻለም ።

ይኸንንም የኢትዮጵያ ነገሥታት ስለተረዱት አንዳንድ ጊዜ የእስላሞቹ ባለሥልጣኖች የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳስ ሲያስሩ በኢየሩሳሌም ገዳም ያሉትን መነኮሳት ወይም ከዚህ ሊሳለሙ የሚሄዱትን ኢትዮጵያውያንን ሲያንገላቱ እነርሱም በውስጣቸው ያለውን እስላም ሲያጉላሉ ይልቁንም ለግብፅ ሕይወት የሚሰጠውን ከጣና ሐይቅ የሚወጣውን የዓባይን ወንዝ ገድቦ ለማስቀረት ሲያስፈራሩ ኖረዋል ።

ከነዚህ ነገሥታት ውስጥ ዓባይን በመገደብ የግብፁን ሡልጣን በማስፈራራት በጽሑፍ አልፎ አልፎ ስማቸው ተጠቅሶ የሚገኙት ነገሥታት ቅዱሳን የተባሉት የዛጕዬዎቹ ዓፄ ላሊበላና ዓፄ ነአኩቶ ለአብ ፣ ሸዋ የነበሩት ዓፄ ሠይፈ አርእድ ዓፄ ዳዊትና ዓፄ ይስሐቅ ናቸው[ካ]ለምሳሌ ቸሩሊ ባሳተሙት በዚህ መጽሐፍ ላይ የግብፁ ሡልጣን የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስን ቀረጥ ከፈሉ ብሎ ባሠረ ጊዜ የዓባይን ፈሳሽ ዓፄ ዳዊት ስላገደ የግብፁ ሡልጣን የጌታችንን ግማደ መስቀልና ሌላም ገጸ በረከት መላኩን ለማስረዳት በግዕዝ እንደዚህ ይላል ።

"ወውእቱ ዳዊት ዘሜጠ ለፈለገ ዓባዊ ከመ ኢይረድ ግብፅ በምክንያት ዘሞቅሐ ንጉሠ ግብፅ ለአባ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘለ እስክንድርያ በምክንያተ ጸባሕት ፣ ወበይነዝ ፈነወ ሎቱ ንጉሠ ግብፅ አምኃ ለዳዊት ንጉሥ ግማደ መስቀሉ ለክርስቶስ" (1) ።

ይሁን እንጂ እንደዛሬ ቴክኒካዊ መሣሪያ ባልበዛበት ዘመን ዓባይን የሚያህል ውኃ ከለመደው መስመሩ ቀልሶ ወደ ሌላ መውሰዱ አስቸጋሪ ስለሆነ አብዛኛው ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታት የኃይሉን ነገር እየተዉ ጳጳስም ላገራቸው ለማስመጣት ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱትን ኢትዮጵያውያን ጉዞ ለማቃናት ለግብፅ ሡልጣኖች ገጸ በረከት እየላኩ የወዳጅነት ግንኙነት ሲሞክሩ ኖረዋል ።

በዚህ ምክንያት እ. አ. አ. ፲፫፻፲፪ - ፲፫፻፲፫ ዓ. ም. ባዒ ዓምደ ጽዮን ጊዜ ለመሐመድ ኢብን ካላኡን ባዔ ይስሐቅ ጊዜ በ፲፬፻፳፫ ዓ. ም. ለሡልጣን ባርሳቤይ ባዒ ፹፩ ለሡልጣን ካይትባይ መላክተኛ ከኢትዮጵያ ወደ ካይሮ እየተላከ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ከተመላለሰ በኋላ ከ፲፬፻፹፩ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ድረስ

(1) Etiopi in Palestina. ፩ኛ ቮሊዩም ገጽ 267

ይኸውም ማለት ካፄ እስክንድር ዠምሮ እስከዚህ እስካፄ ልብነ ድንግል ድረስ ግን ኙነት ተቋርጦ መኖሩን አሁን ግን ንግሥት እሌኒና ዓፄ ልብነ ድንግል ወደ ካይሮ ወደ ሱልጣን ወደ አል ማሊክ አል አስራፍ ቃንሹህ አል ጋውሪ እ. ኤ. አ. በ፲፭፻፲፮ ዓ.ም. መላክተኛ መላካቸውን ኢብን ኢያስ የሚባለው ግብፃዊ በዓረብኛ ጽፎ ካኖረው ላይ ሙሴ ኤንሪኪ ቸሩሊ ወደ ኢጣሊያ ተርጕመው ከዚህ በፊት በጠቀስነው መጽሐፍ አሳትመውታል (1) ። እርሳቸውም ከዚህ በፊት ካህል የሚባል የጀርመን ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፴፱ ዓ. ም. ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዓይነት ማሳተሙን ገልጸዋል ። «ሐሙስ ፳፫ ሙሐራም ፱፻፳፪ ሒጅራ (Mars 1516) የኢትዮጵያ ንጉሥ የመላክተኛ ጓድ ካይሮ ደረሰ ። ጓዱም የሚሄደው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ነው ። ግን ካይሮ የመጣው ከግብፁ ንጉሥ ወደ ፓለስቲን ለማለፍ አስፈላጊውን ፈቃድ ለማግኘት ነው ።»

በተረፈ ራሳቸው ሙሴ ቸሩሊ ስለጠቅላላው አቀባበል በሙሉ ከዓረብኛ ወደ ኢጣሊያንኛ የተረጐሙትና አሁን እኔ ወደ አማርኛ የምመልሰው የደብዳቤው ዋና ፍሬ ነገር እንደዚህ የሚል ነው ።

«ሐሙስ ፲፰ የኢትዮጵያ ንጉሥ መላክተኛ ደረሰ ። ከብዙ ጊዜ ዠምሮ የሐበሻ ንጉሥ መላክተኛ ወደ ግብፅ አልመጣም ነበር ። በፊት አንድ የኢትዮጵያ መላክተኛ በአል ማሊክ አል አስራፍ ካይትባይ ዘመነ መንግሥት መጥቶ ነበር ። ከዚያ ወዲህ ከዚህ ካሁኑ በቀር ሌላ መላክተኛ አልመጣም ። መሬታቸውም ሩቅ ነው ። ከግብፅም ጋር ምንም ጉዳይ የላቸውም . . . . ሱልጣኑ እነርሱን ሲቀበል ባንድ ከፍተኛ ቦታ ሆኖ ግራና ቀኝ ኤሚሮቹ እንደማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር . . . መላክተኛው ከርሱ ጋር አምስት ከአበሻ ትልልቅ ሰዎች ውስጥ ተከትለውት ነበር ። ከዚያ ሌሎችም ታላቅነት የሌላቸው ነበሩ . . ከመካከላቸው ራሱ ባዶ ሆኖ የተገለጠ የለም ። ጕፈር አድርገው ነበር ። ግማሾቹ ትልልቅ ሎቲና አምባር አድርገዋል ። የመላክተኞቹ መሪ ያንድ መስፍን ልጅ ነው ይባላል ። አባቱም ከዚህ በፊት በሱልጣን ካይትባይ ዘመነ መንግሥት (በአፄ እስክንድር ጊዜ) መጥቶ የነበረው ነው ይባላል ። እርሱም በራሱ ላይ በቀይ ከፋይ ፥ በወርቅና በከበረ ድንጊያ የተጌጠ እንደ ቆብ ያለ ደፍቷል ። በቆቡ ላይ ዋጋው ውድ የሆነ ሉል አለው ። በቀለም ያጌጠ የሐር ልብስ ለብሷል ፤ የቀሩትም እንደ ማዕርጋቸው . . . . . በድምሩ የመጣው ሰው ቍጥሩ ፲፱ ሰው ነበረ ። ወገባቸውን በነጭ ሻሽ (መቀነት) አስረዋል ። ከሠፈራቸው ተነሥተው ሲመጡ የሚመሩዋቸው በግመል የተጫኑ ሁለት ነጋሪት አሉዋቸው ። ከነርሱም ጋር ፓትርያርካቸው (ጳጳስ ወይስ አንድ የተከተለ የቤተ ክህነት ባለሥልጣን ?) ከጀርባው በኩል በወርቅ የተጠለፈ አረንጓዴ የሐር ካባ ለብሶ ይታያል ። በካይሮ ያለው ሁሉ ክርስቲያን በደስታ ሊቀበላቸው ተሰለፈ ። አለቆቹ (የሐበሾቹ) በፈረስ ሲጓዙ የቀረው ሕዝብ በእግሩ ነው . . . . . ዋንዬው ከሁሉ ፊት ቀድሞ ይጓዛል ።

(1) Etiopi in Palestina ፩ኛ ቮሊዩም ገጽ 301 - 388

ከቤተ መንግሥቱ በሩፍ ሲደርሱ ሪኸርም ከብረት የተሠሩ መቀመጫዎች ከሡልጣኑ ፊት ሲደርሱ የሚቀመጡበት ይዘው ነበር ። ነገር ግን የኑብያዎቹ ሹማምንቶች አልፈቀዱላቸውም ። ይህ ነገር ከዚህ በፊትም በአል ማሊክ አል አሽራፍ ካይትባይ ጊዜ ደርሷል ። እንደዚሁ መቀመጫቸውን ይዘው መጥተው ሳለ ከሡልጣኑ ፊት ለመቀመጥ አልፈቀዱላቸውም ። ከሡልጣኑ ፊት ሲደርሱ መሬት ሳሙ ..... ሦስት ጊዜ መሬት እየሳሙ ቀርበው ከሐበሻው ንጉሥ የተላከውን ደብዳቤ አስረከቡ . . ።

ደብዳቤው ለሡልጣኑ ተነበ በውስጡ ሡልጣኑን የሚያሞጋግስና የሚያወድስ አለበት ። ቀጥሎም መላክተኞቻችን ወደ ግብፅ የመጡት ኢየሩሳሌም ሄደው ቅዱስ መቃብርን ለመጎብኘት ነውና እንዳይከለከሉ'' ይላል ። ወረቀቱም ሲነበብ ፳ ደቂቃ መላክተኞቹ እንደቆሙ ነበሩ ።

ከዚያ ተመልሰው ወደ ከተማው በታች ወረዱ በሡልጣኑ ትእዛዝ እስኪሄዱ ድረስ ሰፈራቸው አንበሶች ድልድይ አጠገብ ከግመሎች አደባባይ ነበር ። ወደነር ሱም ሠፈር ሰው እንዳይገባ የሚከለክሉ የማመሉክ ዘበኞች በሩቀን ይዘው ይጠብቁ ነበር ። ከቤተ መንግሥቱም ወደ ሠፈራቸው ሲሄዱ ዋሊና ሚሀማንዳር (ባል ደረቦች ሹሞች) የኑብያን ወታደር ይዘው ሕዝቡ ደንገጾ እየወረወረ እንዳይመታቸው ይጠብቋቸው ነበር . . መላክተኛው ግብፅ ለመድረስ ዘጠኝ ወር ተጓዘ ይባላል ። ISIC

መላክተኛው ለሡልጣኑ የላከው ገጸ በረከት ዝቅተኛ ነበር ። በግምት ፲ሺ ዲናር የሚያወጣ ወይም ከዚህ ያነሰ ዋጋ ያለው ነበር ። ሡልጣኑ ባየው ጊዜ ያተረበለትን ሰውዬ ሰደበው ። ከዚህ በፊት ከኢትዮጵያ ነገሥታት ለቀድሞዎቹ ሡልጣኖች ለአል አሽራፍ ባርስባይ ፤ ለአል ዛሂር ክንማክ ፤ ለአል አሽራፍ ካይትቤይና ለሌ ሎቹ የመጣው የገጸ በረከት ዝርዝር ቀርቦ ተነበበለት . . . ከቀድሞዎቹ ነገሥታት ሥልጣን ያሁኑ ዝቅ ብሏል ። አንዳንድ ባለታሪኮች እንደሚሉት የቀድሞዎቹ ነገሥ ታት በአባይ ወንዝ አቅራቢያ ፳ መንግሥታት (የሚገዟቸው) ነበሯቸው ...... አሁን ግን ያሁኑ ንጉሥ ከፊተኛው መንግሥት ደክሞአል ። ከነዚያ ነገሥታት አንዱ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ለመሐመድ ኢብን ካላኡን የላከው ገጸ በረከት የተገመ ተው ከአንድ መቶ ሺ ዲናር ይበልጣል . . . . .።

መላክተኛው በአደባባይ ፫ ቀን ከቆየ በኋላ ከነጓዙ የቅዱስ መቃብርን ቤተ ክርስቲያን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።» ሲል እዚህ ላይ ይቆማል ።

በዚህ በኢብን ኢያስ አጻጻፍ ላይ የምንረዳቸው ብዙ ነገሮች አሉ ። እነሱም

ሀ. የግብፁ ሡልጣን አል ጋውሪ ያደረጉላቸው አቀባበል ከመተገቀሁ በተር ከሩቅ አገር ፺፱ ሰው አስከትሎ የራሱን ወንበር ይዞ ለመጣው ለዋናው ኢትዮጵያዊ መላክተኛ እንኳን ከፊቱ እንዲቀመጥ ሳይፈቅድለት መቅረቱን ።

ለ. ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ሕዝቡ ደንጋያ እየወረወረ እንዳይደበድባቸው በዘበኛ ይጠበቁ ነበር ሲል ሕዝቡ በተለይ የእስላሙ ወገን በኢትዮጵያውያን ላይ ጥላቻ እንደነበረው በነርሱ አንጻር ግን ክርስቲያን የሆነው የሃይማኖት

ወንድምነት እየተሰማው በደስታና በናፍቆት እንደተቀበላቸው ።

ሐ. አፄ ልብነ ድንግል ለሥልጣን አል ጋውሬ የላኩት ገጸ በረከት አባቶቻቸው እነ አፄ ዓምደ ጽዮን ለሹመት አባቶቹ ከላኩት ያነሰ በመሆኑም ተናዶ አቅራቢውን መሳደቡን ።

መ. የዱሮ ባለሥልጣኖቻችን ወደሩቅ አገርም ቢሆን ሲሄዱ የራሳቸውን መቀመጫ (ወንበር)ና ነጋሪት አሲዘው መሄዳቸውን ።

ሠ. የመላክተኞቹ አለቃ የለበሰው ልብስ የሐር ቀይ ልብስና የደሩው ቆብ በክፈይና በወርቅ ያጌጠ ነው ሲል ታላቅ የቤተ መንግሥት ሰው ወይም አንድ ባለነጋሪትና ራስ ወርቅ ያሰረ መስፍን መሆኑን ።

ረ. የመላክተኞቹ ቍጥር ፮፻ ሙቶ ይደርሳል ሲል በዚያን ጊዜ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ከዛሬ ጊዜ የበለጠ ይታሰብበት እንደነበረ ያስረዳናል ።

በዚሀ መካከል ልናስታውስ የሚገባው ሡልጣኑ የመላክተኞቹን አለቃ እፊቱ አስቀምጦ ሳያነጋግረው መቅረቱ አይደለም ። በውነቱ የኛም ነገሥታት ከውጭ አገር ለመጣ መላክተኛ የሚያደርጉት አቀባበል ከሡልጣኑ የሚሻል አይመስልም ። ይኸንንም አፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋሉ ንጉሥ መላክተኛ ለሮድሪግ ደሊማ ወደፊት የሚያደርጉትን አቀባበል ስንመለከት በሰፊው እንረዳዋለን ።

ነገር ግን የሚያሳስበን ክርስቲያኑ ወገን (ግብፃዊ) በደስታና በናፍቆት ኢትዮጵያውያኑን ሲቀበል የእስላሙ ወገን በደንጊያ ለመቐቐት ያስፈራራበትና የዘበኛ ጥበቃን ያስከተለበት ምክንያት ነው ። ምናልባት ከዚህ ምዕራፍ ቀጥሎ እንደምናነበው በዚሁ ዓመት እ.አው.አ. ፲፭፻፲፮ (እንደ ኢ.ት. ፲፭፻፰) ዓ.ም. ዓፄ ልብነ ድንግል ከአዳሉ ባላባት ከማኅፉዝ ጋር ተዋግተው ባላባቱን አባ እንድርያስ የሚባሉት መነኵሴ አንገቱን ቆርጠው ግዳይ ጥለውበታል ። እርሱም በዓረቦችና በግብፆቹ ዘንድ የታወቀ ስለሆነ ልብስም ባንዲራም የጦር መሣሪያም እየላኩ አደርጅተውት ነበርና የመሞቱና አንገቱን የመቆረጡ ወሬ በካይሮ በመሰማቱ ሕዝቡ ተናዶ ይሆን ? ወይስ ከዚህ ጋር ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ከክርስቲያኑ የፖርቱጋል መንግሥት ጋር በእስላሞቹና በግብፆቹ ላይ ውስጡን መላላኩ ተሰምቶ የዚህ ቍጭት ይሆን ? ነገር ግን ኢብን ኢያስ መላክተኞቹ ካይሮ ደረሱ የሚለው በመጋቢት ሲሆን እንደ አልቫሬዝ አጻጻፍ ዓፄ ልብነ ድንግል ማኅፉዝን የወጉት በሐምሌ ወር በዚሁ ዓመት ስለሆነ ጥላቻን የፈጠረው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር በማቴዎስ አማካይነት የተወጠነው ግንኙነት ሳይሆን አይቀርም ። ይኸንንም አልቫሬዝ በመጽሐፉ ምዕራፍ ፩፻፳፱ ላይ ከኢየሩሳሌም ከተመለሱት ከኛው ሰዎች ላይ መስማቱን አብራርቶ ገልጾታል ።

የኢብን ኢያስ መጽሐፍ የመልክተኞቹን አለቃ የመስፍን ልጅ ነው ከማለት በቀር ስሙን አልጠቀሰውም ። ሙሴ ቼሩሊ ስለነዚሁ መልክተኞች ሰነድ ከያለበት ሲያጠራቅሙ መዝገበ አክሱም Liber Axum በሚባለው መጽሐፍ ላይ «በ፲፭፻ወ፰ ዓ. ም. ወረዱ ኢየሩሳሌም ሠራዊተ ንጉሥ» የሚል ቃል አግኝተው ከዚያ ደግሞ ንጉሡ ልብነ ድንግል የከረምትን ወራት እንዶጥና ከሚባል ሥፍራ ባሳለፉበት

ሁለት ጊዜ አንድ ጊዜ «ወረዱ አሥራተ ኢየሩሳሌም» ሲመለስ ደግሞ «ተመይጡ አሥራተ ኢየሩሳሌም» የሚለውን ቃል ጠቅሰዋል ። አዲ ንእግን የሚባል በጻፈው ዜና መዋዕል ደግሞ «በ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. ወልደ ዓምደ ሚካኤል ወከንቲባ ዳፍላ ሖሩ ኢየሩሳሌም በትእዛዘ ንጉሥ» በሌላ ጽሑፍ ደግሞ ለነዚሁ ወደ ኢየሩሳሌም ለተላኩት ሁለት መኳንንት ወይም አንድ መስፍን አንድ መኰንን ለከንቲባ ዳፍላ የአምባ ዶርሖንና የባቅላን መሬት ወደ ኢየሩሳሌም ለተላከበት ዋጋው (በእንተ ንግደቱ ለኢየሩሳሌም ለወልደ ኃራግደይ (ዓምደ ሚካኤል ?) የአድገብሱን አገር ነዋሪ ተመላላሽ መልክተኛ (ከመ ይኩን ነጋዲ) ይሆን ዘንድ ንጉሡ በጉልትነት መትከላቸውን ገልጸዋል ።

ሙሴ ቼሩሊ እንደተገነዘቡት በፊተኛው ላይ ወልደ ዓምደ ሚካኤል ካለ በኋላ ርስት አተካከሉ ላይ ወልደ ኃራግደይ ያለው እንዱን ሰው መሆን አለበት ። ይኸውም ዓምደ ሚካኤል የመጠሪያና የመጽሐፍ ስም ኃራግደይ (ወታደር ገዳይ) የጉብዝና ወይም የፈረስ ስም ይሆናል ።

እንግዲህ እንደሚመስለው ዋናው መልክተኛ ራስ ወርቅ ያለው የዓምደ ሚካኤል ልጅ ፡ ምክትሉ የሐማሴኑ ሹም ከንቲባ ዳፍላ ይሆናል ። የተሰጠውም የጉልት አገር ከዚያው ኤርትራ ውስጥ ነው ።

ነገር ግን ዓምደ ሚካኤልስ ማነው ? ወደ ኢየሩሳሌም የመልክተኞች አለቃ ሆኖ የተላከው መስፍኑ ልጁስ ማነው ? ባዬ ናዖድና ባዬ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ውስጥ በዓምደ ሚካኤል ስም የሚጠሩ ብዙ መኳንንት አሉ ።

ሀ. ቢትወደድ ዓምደ ሚካኤል (አንዳንድ ጊዜ ራስ ዓምዱ) ባዬ እስክንድር ጊዜ መንጋ (ወገን) ተነድቶበት የሞተ ። ባዬ ናዖድን ንግሥ ተቃውሞ ስለነበረ በዚሁ ከእንገቱ በታች

ለ. ዓምደ ሚካኤል (የጺሕፈ ላም ሮቤል ልጅ) ወደፊት በግራኝ አህመድ ጦርነት ከአቡበክር ቀጢን ጋር ሲዋጋ አብድ ኢን ናስር የገደለው ፣ ዝግንነቱ በእስላሞች ዘንድ የተደነቀው አለ ። ነገር ግን የሞተው ባባቱ እግር እንደተተካ በወጣትነቱ ጊዜ ስለሆነ የርሱ ልጅ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር ለማለት አይቻልም ።

ሐ. ራስ ዓምዱ (ዓምደ ሚካኤል) ወደፊት እንደምናነበው በግራኝ ጊዜ ወደፊት ሲዋጋ በአዳሙ እጅ የሞተው ።

ይህ የመጨረሻው ራስ ዓምዱ ወይም ዓምደ ሚካኤል የልጁ ስም ቢትወደድ ሠርጼ ይባላል ። እርሱም የንጉሡን እኅት ያገባ ንጉሣዊ ቤተሰብ ስለሆነ ምናልባት ራሱ የመስፍንነት ዘር ባይኖረው ያው እንደ መስፍን የሚቆጠር ነው ። ቢትወደድ ሠርጼ በግራኝ ጦርነት ብዙ ጊዜ በመዋጋት የታወቀ ሰው ነው ። በተለይ በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. አምባ ግሼን የተከበበ ጊዜ ከንጉሡ ዘንድ ጦር ይዞ ሄዶ ተዋግቶ ዋናውን የጦር መሪ ገራድ አሕሙሹን ማርኮ ለአማቹ ንጉሥ ላኜ ልብነ ድንግል ግዳይ በመጣል አስደስቷል ። ነገር ግን ይህ የጦር አለቃ ወደ ኢየሩሳሌም ለመላኩ ምንም አስረጅ ጽሑፍ የለም ።

ነገር ግን ባንድ ወገን ደግሞ የግዕዙ መጽሐፋችን ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳቸውን «ወረዱ አሥራተ ኢየሩሳሌም» መመለሳቸውን ለማስረዳት «ተመይጡ አሥራተ ኢየሩሳሌም» ያለውና ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በበኩሉ በመጽሐፉ ምዕራፍ ፻፳፫ ላይ ከሚተርከው ጋር ይመሳሰላል ። አልቫሬጽ በዚሁ ምዕራፍ ላይ “ ...... ገጸ በረከቱን ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ ያስረከበ አሁን የንጉሡ ነገሥቱን እኅት የሚጠብቅ አባ አሥራት የሚባል ሰው ነው” ይላል ስለዚህ ምንም እንኳን የዓምደ ሚካኤል ልጅ መሆን አለ መሆኑን ባይገልጽ በእርግጥ መልክተኞቹን ይዞ በካይሮ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ይኸው አሥራት ይሆናል ።

እንደዚሁም አልቫሬጽ በምዕራፍ ፻፳፱ ላይ ከሐማሴን እስከ ሱዋኪን ድረስ ያለውን አገር ከባሕር ነጋሹ በታች ሆነው የሚገዙ ቃፍላና ዳፍላ የሚባሉ ሁለት ሹማምንቶች መኖራቸውን ስለሚያረጋግጥ በመልእክቱ ስላስደሰተ የባቅላን የጓደኛውን መሬት በጉልትነት ለዳፍላ ተክለውታል ማለት ነው ።

ምዕራፍ ፲፭

ከዓረቦች ወረራ በኋላ የቱርክ የቄሣር ግዛት - ግብጽ በቱርኮች እንደተወረረች - የግብፅ የመጨረሻው ሱልጣን ቱማን በቱርኩ ሱልጣን በሰሊም ትእዛዝ ተሰቅሎ እንደሞተ ፣ ፲፭፻፲ ዓ.ም.

ባለፈው ጊዜ በየአጋጣሚው ምክንያት ስለቱርክ መንግሥት ባጭሩ ጠቅሰን አልፈናል ። አሁንም የፖርቱጋልን ሁኔታ ካመለከትን በኋላ የርሱና የኛም ባላጋራ የሆነውን የቱርክን አመሠራረት የግዛቱን ስፋት የግብፅን አወዳደቅ መመልከት የታሪኩን መንገድ ይበልጥ ሊያብራራልን ይችላል ።

መሐመድ በሰባተኛው መቶ ዓ.ም. ላይ የእስላምን ሃይማኖት ከመሠረተና የዓረብን አገር የውስጥ አንድነት አቋቁሞ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ያቋቋመው የውስጥ አንድነትና የመሠረተው ሃይማኖት ሊጠፋ አልቻለም ። እንዲያውም ከርሱ ቀጥለው የተሾሙት እነከሊፋ አቡበከር ፣ እነከሊፋ ኡመር ፣ እነከሊፋ ኡስማን ፣ እነከሊፋ አሊና ተከታዮቻቸው ከነበራቸው ግዛት ከዓረብ አገር ውጭ እየወጡ የአፍሪካ ሰሜንና ታናሽ እስያን በመሣሪያ እየተዋጉ በአንደበት እየሰበኩ ግዛታቸውንና ሃይማኖታቸውን በማጣመር አስፋፉ ። ከዚያም እስከ ኤስፓኝና እስከ ፈረንሳዊ ደቡብ ድረስ መዝለቃቸው በየታሪኩ የተረጋገጠ ነው ።

የክርስቲያኖች መሪና ተስፋ የሆነው የቁስጥንጥንያ መንግሥት ከምዕራብ መንግሥታትና ከሃይማኖት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ባንድ ወገን ከፋርሶች በሌላው ወገን ከሞንጐሎች ከጠላቶቹ ሲከላከል ኃይሉ ስለተበታተነና ስለደከመ እስፈሪውን የእስላምን እርምጃ ለማቆም አልቻለም ። ወደ መጨረሻ ግድም በዓረቦቹና በፋርሶቹ ፣ በፋርሶችና በሞንጎሎች መካከል ከ፲፪፻፰ - ፲፫፻፶፱ ዓ. ም. ድረስ ብዙ ዘመን ጦርነት ከተደረገ በኋላ ዓረቦቹን ፋርሶች ፋርሶቹን ሞንጎሎቹ ሞንጎሎቹን ቱርኮች እያጠ

ቋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ መጥተው በዚህ በ፲፭ኛው መቶ ዓ. ም. መገባደጃ ላይ የመጨረሻው አሸናፊ የቱርክ ሕዝብ ሆነ ። የዚህም ሁሉ የጦርነት ሒደት ከመስቀል ጦርነት ወዲህ እርስ በርሳቸውም ከክርስቲያኖቹም ጋር ያደረጉት ጦርነት ታሪኩ ብዙ ነው ። ስለዚህ አሁን ሁሉንም ትተን የኛን መንግሥት ስለሚመለከተውና ባዔልብነ ድንግል መንግሥት ዘንድ ተስፋ የተጣለበት የፖርቱጋል ዋና ባላንጣ ስለሆነው ስለቱርክ መንግሥት አነሣሥ ብቻ እንመልከትና ወደ ፖርቱጋሎቹ እንመለሳለን ።

ቱርኮች ከሺ ዓመት በፊት ተበታትነው ሲኖሩ በ፩ሺ፩፻ ዓ. ም. ውስጥ ማግ ሾቹ በፋርስ አጠገብ ገሚሶቹ አሁን ባሉበት በቱርክ ውስጥ ለየጎሳቸው በንጉሦቻቸው እየተገዙ ሲኖሩ በታላቁ የእስላም ግዛት ላይ ዓረቦች ቀጥሎ ፋርሶች ከዚያ ሞንጎሎች ከተስፋፉበት በኋላ በመጨረሻ ከቱርኮች ባላባት ውስጥ ኦትማን (ኡስማን) የሚባለው የቶግሩል ልጅ መንግሥቱን በደንብ አቋቁሞ በሺ፫፻ ዓ. ም. ላይ የቱርክን መንግሥት መሠረተ ። ከርሱ ቀጥለው ታላላቅ ነገሥታት (ሱልጣኖች) በቱርክ ዙፋን ተቀምጠው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየሉ ቀድሞ ዓረቦችና ፋርሶች ይዘውት በነበረው ሰፋፊ የታናሽ እስያና የአፍሪካ ሰሜን ግዛት ተመሥርተው በነሶሊማን ፩ኛ ፤ በነሙራድ ፪ኛ ጊዜ (፲፫፻፶ - ፲፭፻፲፯) የግሪክ የሐንጋሪ ግዛቶች በጦርነት ተወስደው የእነዚህ ሁሉ አገሮች የክርስቲያን ነገሥታት ለእስላሙ መንግሥት ሱልጣኖች እየታዘዙና እየገበሩ [illegible]ር ግዞት ሆነባቸው ።

ከምዕራብ የአውሮፓ የክርስቲያን ነገሥታት ከፖርቱጋል ፤ ከኢስፓኝ ፤ ከፈረንሳይ ፤ ከጀርመን መንግሥታት ጋር ተባብረው የቱርክን መንግሥት እንዳይመልሱ በመካከላቸው አንዱ ያንዱን ግዛት ለመያረብ ሲፈልግ አንዱ በሌላው የዘውድ አገር ተወላጅነትን እየጠቀሰ ዘውዱን ለመውረስ በመጣጣር እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ስምምነት አልነበራቸውም ነበር ። የሃይማኖት አባታቸው የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለማስማማት ቢሞክሩ አልሆንላቸውም ። በነርሱም አለመስማማት የቱርክ ባለሥልጣኖች ደህና አድርገው ተጠቀሙበት ።

ብዙ ከአውሮፓ ፤ የግሪክ ፤ የቡልጋሪ ፤ የሐንጋሪ ፤ የዳልማስያ ፤ የጀርመንና የኦትሪሽ ተወላጆች በብዛት ወደ ቱርክ መንግሥት እየገቡ ግማሾቹ ጥበብ አስተማሪ እየሆኑ የቀሩትም በወታደርነት ድርጅት ውስጥ እየገቡ ሹማምንትም ወታደርም እየሆኑ ቀድሞውኑ የደረጀውን የቱርክን መንግሥት በዕውቀትም በወታደርም ይበልጥ አደረጁት ። በ፲፬ኛውና በ፲፭ኛው ዓ. ም. ላይ እንደ ዕድል በቱርክ መንግሥት ዙፋን ላይ የሚወጡት ነገሥታት ብልኅነት የአስተዳደር ዘዴ ፤ የድል አድራጊነት ዕድል የተሰጣቸው ገናና ስመ ጥሩ ስለሆኑ የነበራቸውንና አዲስ የሚገዛላቸውን ሕዝብ በሀብት ፤ በሹመት ፤ እያሳደጉ ታላላቅ ሹማምንት በየአውራጃው እየላኩ የቱርክን ግዛት ያስፋፉ ገባ መር ።

ከቱርክ ሱልጣን ከሙራድ ፩ኛ ቀጥሎ ልጁ መሐመድ ፪ኛ ያባቶቹን የገዥነት አርአያ በመከተል እንዲያውም ከነርሱ የበለጠ በመሥራት እስከዚህ ድረስ እየተከላከለ የቆየውንና የደከመውን የቊስጥንጥንያን መንግሥት በፍጹም ለመያ

ምስስ ተነሣ ። ስለዚህ የቁስጥንጥንያን ከተማ ከቦ ብዙ ቀን ከወጋት በኋላ እ.አው.ቀ.
በ፲፬፻፶፫ ዓ. ም. ቅጥሩን ጥሶ ከተማዋን ያዛት ። ቆስጠንጢኖስ ፲፩ኛው የሚባለው
ክርስቲያኑና የመጨረሻው የቍስጥንጥንያ ንጉሠ ነገሥት በከተማው ባንደኛዪቱ
መንገድ ላይ ሲዋጋ ከተማው ተቃጥሎ ጭሱ በሚጨስበት መካከል የተዋጋበትን
ሰይፍ እንደጨበጠ ሞቶ ተገኘ ። በዚህ ምክንያት እስከዚህ ጊዜ ድረስ የቱርኮቹ
መደበኛ ከተማቸው የነበረው አንድሪኖፕል ቀረና ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የሱልጣኖቹ
ዋና መቀመጫ የሰፊው ግዛታቸው መናገሻ ከተማ ቍስጥንጥንያ ሆነች ።

ይህች ከተማ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ከመሠረታት ዠምሮ እስከዚህ ጊዜ ድረስ
የክርስቲያን ነገሥታት መናገሻ ፤ የክርስቲያን ሃይማኖት ዋና መደብ የነበረችው
በክርስቲያኖቹ ነገሥታት የርስ በርስ ጠብ የተነሣ የቱርኮች ዋና መናገሻ ከተማ
ሆና ስሟም እስጣምቡል እየተባለ ይጠራ ዠመር ።

ታላቁ የምሥራቁ የክርስቲያን መንግሥት ቍስጥንጥንያ እ.አው.ቀ. ፲፬፻፶፫
ዓ. ም. በወደቀበት ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ነበሩ ። ከወ
ዲያ ቱርኮች በገነኑበት ዘመን ከዓምደ ጽዮን ዠምሮ የአዳል ባላባቶች ከኢትዮጵያ
ንጉሠ ነገሥት ግዛት ለመውጣት ወይም ደቡቡንና ምሥራቁን ኢትዮጵያ እጅ ለማ
ድረግ እነነስረዲን ፤ እነሐቀዲን ፤ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ፤ እነመሐመድ በድላይ ካፄ
ዘርዓ ያዕቆብ ጋር እየተዋጉ መሸነፋቸው የሚታወስ ነው ። በዚህ ዘመን ቱርክ ስለ
ተጧነ ግብፅና የዓረብ አገሮች በኢትዮጵያ የተነሡትን እስላሞች ለጊዜው እንደ
ልብ ሲረዷቸው አልቻሉም ነበር ። ያለዚያ የግራኝ አህመድ ጦርነት ምንም እን
ኳን ግራኝ ገና ወጣት ቢሆን ቀደም ብሎ ሊነሣ በቻለ ነበር ።

ግራኝ አህመድ ባፄ ልብነ ድንግል ላይ በተነሣበት ዘመን ፲፭፻፲፱ - ፲፭፻፴፮
ዓ. ም. ላይ የቱርክ ኀኝነት የግብፅ ተገኝነት ተደላድሎ ስለነበረ ግራኝ በዚህ ጊዜ
ጦርነቱን ለማንሣት ምቹ ሆነለት ። ግራኝ ጦርነቱን ባነሣበት ጊዜ የቱርክ ሱል
ጣን ማን ነበረ ብለን ለማወቅ የፈለግን እንደሆነ ሱልጣን ሶለይማን ሆኖ እናገኘዋ
ለን ። እርሱ የቱርክ ንጉሠ ነገሥት የሆነበት ጊዜ እ.አው.ቀ ፲፭፻፳ - ፲፭፻፷፮ (እንደ
ኢ.ት. ፲፭፻፲፪ - ፲፭፻፶፰) ዓ. ም. ነው ። ይህ ያንዱ የሶለይማን ዘመነ መንግሥት ያፄ
ልብነ ድንግልንና የልጃቸውን ያፄ ገላውዴዎስን ዘመነ መንግሥት በሙሉ አጠ
ቃሎ ይዞታል ማለት ነው ።

በዚህ መካከል እኛን በፖለቲካም በጥቅምም በጉርብትናም በሃይማኖትም
ይኸውም ጳጳስ በማስመጣቱ ጉዳይ በኢየሩሳሌም ጉዞ የሚያገናኘን ግብፅ ራሱ ከዓ
ረቦች ወረራ ወዲህ የእስላም መንግሥት ስለሆነ ይማስቆና ባግዳድ ያሉት ከሊፋ
ዎች ሲገዙት ቆይተው በመጨረሻ ከኩርድ የሚወለደው ሳላዲን የአዩቢትን ዲና
ስቲ (ሥርወ መንግሥት) መሥርቶ ነበር ። የርሱም ዘር ከ፲፩፻፷፩ እስከ ፲፪፻፵፱
ዓ. ም. በግዛት ከቀጠለ በኋላ ለነገሥታቱ ተወላጅነታቸው የቱርክ የሆነ የዘበኛ
ጦር ነበራቸው ። ስማቸውም ማመሉክ - ባሮች ይባላሉ ።

እነዚህም የመጨረሻውን ሱልጣን የማሊክ ሳሊህን ልጅ ገድለው ከነርሱ መካ
ከል አይባክ የሚባለውን በ፲፪፻፶፬ ዓ. ም. አነገሡና የማመሉክ ወገኖች ሱልጣን እየ

ተባሉ ቱርክ እስኪወሩቸው ድረስ የግብፅና ብዙ ጊዜም የመካከለኛው ምሥራቅ የበላይ ገዥ ሆኑ ። ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንዳመለከትነው የኛ ነገሥታት ዓፄ ዓምደ ጽዮን ፤ ዓፄ ይስሐቅ ፤ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የተላላኩት ከነዚሁ ከማመሉክ ሱልጣኖች ጋር ነው ። በዓፄ ልብነ ድንግል ጊዜ ካይሮ ተልከው የሄዱትን መላክተኞች ደጅ ያስጠና የመላክተኞቹንም መሪ እፊቱ ተቀምጦ እንዲነጋገር ሳይፈቅድ እንደ ቆመ አነጋግሮ የመለሰው ፤ የቀረበለትንም ገጸ በረከት በመናቅ ከፊቱ አንሱ ብሎ የተቆጣው ሙሉ ስሙ አል ማሊክ አል አስራፍ ካንሱህ አል.ጋውሪ (ኤል ጉሪ) የሚባለው ሱልጣን የነዚሁ የማመሉክ ተወላጅ ነው ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው እ. አው.ቀ. በ፲፬፻፶፫ ዓ.ም. የቱርክ ሱልጣን መሐመድ ሁለተኛ የቍስጥንጥንያን ከተማ ከያዙት በኋላ ቱርኮች ወደ ምዕራብ እየገፉ እስከ ቪየና ያለውን የባልካንን አገር በምሥራቅ በኩል የጤግሮስና የኤፍራጥስን ወንዝ እያለፉ ባግዳድን ሞሱልን ያዙ ። በአፍሪካ ሰሜን እንትሪፖሊ ፣ ቱኒዚ ፣ አልዠሪ ከተያዙ በኋላ እ.አው.ቀ. ነሐሴ ፳፬ ፲፭፻፲፮ የግብፅ ወታደር ማርጅ ዳሬቅ ከሚባለው ሥፍራ ላይ አሌፖ (ሶርያ) እጠገብ በሱልጣን ካንሱ አል.ጋውሪ መሪነት ከቱርክ ጦር ጋር ተጋጥሞ ትልቅ ጦርነት አደረገ ። ቱርኮች በመድፍና በመሣሪያ ጥራት በአመራርና በጀግንነትም ከግብፆቹ ብልጫ ስለአሳዩ ድል አደረጉና ካንሱ አል.ጋውሪ በጦርነቱ ላይ ሞተ ። ቱርኮችም የሶርያን ግዛትና ከተሞች እነአሌፖን ፤ እንደማስቆን ያዙ ። የISIC ሱልጣን ራሱ ሰሊም ፩ኛ ጦርነቱን ይመራ ነበርና የግብፁን ሱልጣን ካንሱ አል.ጋውሪን ካሸነፈ በኋላ በደስታና በእልልታ ደማስቆ ገባ ። ከዚያ በኋላ ሱልጣን ሰሊም «ርኩሱ ጌታህ ካንሱ በኛ ተመትቶ ተቀጥቷልና አንተም የኛን ምሕረት ትፈልግ እንደሆን በጸሎት ጊዜ ስማችንን አስጠራ . . . ረት ለምን» የሚል የኩራት ደብዳቤ ካይሮ ቀርቶ ለነበረው ለቱማን ጸፈለት ። ቱማን ቤይ የሱልጣን ካንሱ የቅርብ ዘመዱ የካይሮ አገረ ገዥ ነው ።

ስለዚህ የጌታውንና የዘመዱን መሸነፍ ከሰማ በኋላ ምንም ይህ እስፈሪ ደብዳቤ ከድል አድራጊው ከቱርኩ ሱልጣን ከሰሊም ፩ኛ ቢደርሰው ዝም ብሎ የጦር መሣሪያ እየሰበሰበ ቆይቶ ግብፅን ለመከላከል ሲጓዝ በበኩሉ ሰሊም ከደማስቆ ተነሥቶ በጃፋና በጋዛ በኩል አልፎ ታቹን በሲና በረሃ አድርጎ ካይሮ አጠገብ ኤል ካንካ (El Kankha) ደረሰ ። ከዚህ በኋላ የሁለቱ ወገን ጦር ሠራዊት እ.አው. ቀ. ጥር ፳፪ ቀን ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ሬዳኒያ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ተጋጥሞ በኃይል በሚዋጋበት ጊዜ ቱማንም ራሱ በብርታት ሲዋጋ ሱልጣኑን ያገኘሁ መስሎት ሲናን ገደለው ። የሆነ ሆኖ የመድፈኛው ክፍል እንደጠበቀው ሳይዋጋለት ስለቀረ ተሸንፎ ወደኋላው ተመለሰና ካይሮን ለመከላከል አሰበ ። ቱርኮችም እግር በእግር እየተከታተሉ ካይሮ ላይ ስለደረሱበት አምስት ቀን ሙሉ በካይሮ ከተማ የቱርክና የግብፅ ወታደር እርስ በርሱ ሲዋጋ ሲጋደል ሰንብቶ የመጨረሻው ድል ያው እንደ መጀመሪያው ጊዜ ለቱርኮች ሆነ ። በዚህም ጊዜ ቱርኮች ፳፯ የግብፅን የማመሉክን ሹማምንትና ወታደሮች እየያዙ አረዱቸው ።

የግብፅን የመጨረሻውን የሱልጣንነቱን ሥፍራ የያዘው ይኸው ቱማን ቤይ እስከሚበቃው ድረስ ተከላክሎ አልሆን ሲለውና ወታደሩ ሲሸነፍበት ዓይቶ የዓባይን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ላዕላይ ግብጽ ለመሸሽ ሲያመራ በወደቀ ዛፍ ላይ ምሣር ይበዛበታል እንደሚባለው በረሃ ያሉት የርሱው ተገዥ የነበሩት የበድዊን ባላገሮች እጁን ይዘው ላሸናፊው ለሱልጣን ሰሊም ወስደው አስረከቡት ። ሰሊም ለመዠመሪያ ጊዜ የጭካኔ በቀሉን በልቡ አቆይቶ በውጫዊ የርኅራኄ መልክ አሳይቶ የታሠረበትን ሰንሰለት አስፈትቶ በአጠገቡ አስቀምጦ በደህና መልክ በፈገግታ ሲያነጋግረው ሰነበተ ይባላል ። እርሱም ምሕረት ያገኘ መስሎት ልባዊ የአገዛዝ ምክር አቀረበለት ።

ነገር ግን ሱልጣን ሰሊም የሸረኝነት ጠባይ የተዋሐደው ኖሮ ስለአስተዳደር ስለአገዛዝ እንደሚፈልገው የሚጠቀመውን ወሬ ከተሸናፊው ከቱማን በዝርዝር ከሰማና ሚጥጦ ከጨረሰ በኋላ ውሰዱና ግደሉት ብሎ ስለአዘዘ በባብ ዙይለህ መግቢያ በር ላይ ሚያዝያ ፳፫ - ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ይህ የመጨረሻው የማመሉኮች ሱልጣን ቱማን ተሰቅሎ ሞተ (1) ።

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የግብፅ ሱልጣኖች የመካከለኛው ምሥራቅ የሶርያ የኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ አውራጃች ጌቶች የነበሩት ተዋርደው ከዚህ ጊዜ ዠምሮ አገራቸው ግብፅ ለቱርክ የቄሣር ግዛት እንደ አንድ አውራጃ ሆነች ። ከቱርክ ሱልጣን ለግብፅ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ የሚሾመው የማዕርግ ስሙ ፓሻ ይባል ዠመር ። ከዚያ አከታትለው ቱርኮች በዓረብ አገር ገብተው ባንዳንዱ አገር ላይ የራሳቸውን ፡ በሌላው ላይ ያገሩን ተወላጅ ይሾሙ ዠመር ። ለምሳሌ በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዋና የግራኝ ረዳት የነበረው የዘቢድ ፓሻ ራሱ የቱርክ ተወላጅ ነበር (2) ።

በዚህ ቱርኮችና ግብጾች በሚዋጉበት ጊዜ መካከል በኢትዮጵያ አፄ ልብነ ድንግል በተድላ በደስታ አገራቸውን በሰላም የሚያስተዳድሩበት ጊዜ ነው ። ይኸውም እ.አው.ቀ.፲፭፻፲፰ - ፲፭፻፳፰ (እ.ኢ.ት.ቀ. ፲፭፻፳ - ፲፭፻፲፱ ዓ.ም.) ነው ። ማኅፉዝ የአዳሉ ሱልጣን እንደ ኢት. ቀ. በ፲፭፻፳ ዓ. ም. (፲፭፻፲፮ ዓ. ም.) ቢነሣባቸው በቀላሉ እንዳሸነፉት በሚቀጥለው ምዕራፍ እናነባለን ። ከዚያ ደግሞ አማቼ ግራኝ ሲነሣ (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) በሰላሙ በተድላውና በደስታው ፈንታ በሚያስገርም አኳኋን በክርስቲያኖቹ ኢትዮጵያውያን ላይ ዘወትር የመሸነፍ አደጋ የአልቂትና የስደት መከራ ሲወርድባቸው ይታያል ።

(1) Histoire de la nation egyptienne - G. Hanotaux ፭ኛ ቅጽ ገጽ 1 - 7

(2) Studi etiopici-1-la lingua e la storia di Harar የቼሩሊ ገጽ 34

ISIC

## ምዕራፍ ፲፮

## የማኅተዝና ያዬ ልብነ ድንግል ጦርነት (፲፫፻፳ ዓ. ም.) - ስለ አባ ገብረ እንድርያስ

የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጒዬ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ በሚባለው በመ ዠመሪያው መጽሐፍ ምዕራፍ ፳፫ ላይ የመሐመድንና የዓረቦችን እነሳስ እንብበ ናል ። ከዚያ ወዲህ በመቅድሙ ላይ እንዳመለከትነው ከ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ እስካሁን እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል መንግሥት ፲፭፻ ዓ. ም. ድረስ ከኡ መር ወላስማ የሚወለዱት ደራደር ፡ ሐቅ አድ ዲን (ሐቀ ዲን) ገማል አድ ዲን ገመልዲን) ሳብር አድ ዲን (ሰብረዲን) ካፄ ዓምደ ጽዮን ጋራ ዓሊ የሰበር አድ ዲን ልጅ (የናስር አድ ዲን ልጅ የሚሉት አሉ) ካፄ ንዋየ ክርስቶስ (ሰይፈ አርእድ) ጋር ሐቅ አድ ዲን ፪ኛ ካፄ ንዋየ ማርያም (ውድም አስፈሬ) ጋር በድላይ ሺሀብ ኡድ ዲን መሐመድ (አርዌ በድላይ) ካፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር መሐመድ ቤን በድላይ ሶለይ ማን አህመድ ካፄ በዕደ ማርያም ጋር ሻምስ አድ ዲን መሐመድ ካፄ እስክንድር ጋር እንደምን ሲዋጉ እንደኖሩ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚ ባለው በ፪ኛው መጽሐፍ በየምዕራፉ ተጽፏል (1) ።

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጦር ሠራዊትና በወላስማ ተከታዮች መካከል በየ ጊዜው የተደረገውን የዚህን ጦርነት ታሪክ የኛ ዜና መዋዕል ጸሐፊና የዓረቦች ጸሐ ፊዎች እነ አል ማክሪዚ ሲተርኩት በተለያየ መልክ ያቀርቡታል ። የኛ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ከግራኝ አህመድ የጦርነት ታሪክ በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተሸንፎ መሸሹን አይጠቅሱም ። አልማክሪዚ ግን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የወላስማ ተከ ታዮች ሐቀዲንን ገማልዲንን ባጭሩ አብዛኞቹን አሸናፊ ኢትዮጵያውያኑን ከመር ገም ጋር ተሸናፊ አድርጎ ያሳያቸዋል ።

እነዚህንም ሁሉ የሚደግፏቸው በበላይ የግብፅ መንግሥት ሆኖ በቅርቡ ደግሞ በማዶ በዓረብያ አገር የሚገኙት የጂዳ የሜካ የዘቢድ ሱልጣኖች ናቸው ።

እነዚህ የአዳልና የይፋት የሐረርጌና የሱማሌ ባላባቶች ከነዚያ ጋር በሃይማ ኖት ፡ በዘር ፡ በጋብቻ ፡ በጥቅም ተሳስረው በጥብቅ ይተሳሰባሉ ። በምጥዋና ይልቁ ንም እነዚህ ከወዲህ ከአገራቸው የሚገኘውን ከብት እህል ቆዳ ባሪያ ሲልኩላቸው እነዚያ ደግሞ ከወዲያ በልዩ ልዩ ጥበብና ጊጥ የተሠራ ልብስና ሸቀጣሸቀጥ መሣሪያ ቅመማቅመም ያቀበሉዋቸው ነበር ። በፖለቲካ ፡ በጥቅም በንግድም ብቻ ሳይሆን መካ መዲናን ለመሳለም እነዚህ የይፋትና ያዳል የሱማሌ ባላባቶች በሄዱ ጊዜ እነ ዚያ በፍቅርና በወዳጅነት ተቀብለው ሊያስተናግዱዋቸው እዚያም በሚከርሙበት ጊዜ እየነሡ መወያየታቸው እነዚህ ጥቃታቸውን ሲያወሩ እነዚያ እያዘኑ አለን ላችሁ ማለታቸው የማይጠረጠር ነው ።

(1) ምዕ. 10 - 16 ፡ 24 ፡ 35 ፡ 48 ፡ 53 አል ማክሪዚ Macrizi Historia Regum ገጽ 17 - 41

ባለፈው ምዕራፍ እንዳነበብነው መቀመጫው ከ፲፬፻፵፮ ዓ.ም. (ኢ.አው.ቀ.) ቊስጥንጥንያ (እስጣምቡል) የሆነው የቱርክ መንግሥትም በሳሊም ፩ኛ የክርስቲያኑን የቊስጥንጥንያን መንግሥት አጥፍቶ በ፲፭፻፲፮-፲፰ ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በግዛቱ በሶርያ ፣ በሊባኖስ ፣ በፓለስቲን ፣ በግብፅ ፣ በዓረብ አገር ከተተካና ሥልጣኑን ከዘረጋ ወዲህ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትንም ምጥዋን ሱዋኪምን እየያዘ በያዘው አገር ላይ ግዛቱንም የእስላምንም ሃይማኖት አጸና ። የፖርቱጋል መንግሥት ከአውሮፓና ከሕንድ ኃይሉን እየቀሰቀሰ በእግርም በመርከብም ቢዋጋው ሊበገርለት አልቻለም ። ንግሥት እሌኒ ወደፖርቱጋል ንጉሥ በላኩት ደብዳቤ የባሕር በር ስለሌለን የመርከብ ወታደር አዘጋጅተን እስላሞቹን ለመቃወም አልቻልንም እንዳሉት ምጥዋ የራሷ የወደብ ከተማ ሆኖ ሳለ በፊት በግብፆች ቀጥሎ በቱርኮች ስለተያዘየቦታው ታሪካዊ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ልትጠቀምበት አልቻለችም ። የፖርቱጋል መንግሥት የመርከብ ጦር ልኮ ላንድ ጊዜ ቢይዘውም የቱርክ ወታደሮች መልሰው እጅ አድርገውታል ።

አሁን ደግሞ ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን ይማም ማኅፉዝ የሚባለው አንዳንድ ጊዜ የሐረር ኤሚር የሚባለው ካፄ እስክንድርና ካፄ ናዖድ ዠምሮ ወደላይ ወደ ይፋት እየወጣ ከክርስቲያኖቹ ጋር እየተዋጋ ከብትም ሰውም እየዘረፈ እየወሰደ ፳፭ ዓመት ሙሉ አስፈርቶ ይኖር ነበር ። በየጊዜውም የግብፆቹንና ይልቁንም የጀዳና የዘቢድ ዓረቦችን ድጋፍ አግኝቶ በሐረር ባላ[illegible]ቱም ላይ የዘይላን ወደብ በራሱ ግዛት ውስጥ አድርጎ በዚሁ ወደብ አማካይነት በኢትዮጵያ ያልታየ አዳዲስ ጠበንጃና ጥይት በየጊዜው ይሰጡት ነበር ። ልዩ ልዩ ልብስና ሽልማት እንደዚሁም አንድ ትልቅ ድንኳንና የነቢዩ የመሐመድ ምልክት ያለበትን አረንጓዴ ሰንደቅ ዓላማ እየላኩለት በማናቸውም ረገድ እንዲደረጅና እንዲቋቋም ይረዱት ነበር (1) ።

ርሱም ለዚህ ሁሉ ስጦታና ርዳታ በበኩሉ ከኢትዮጵያ ወርቅ ፣ የዝሆን ጥርስ ፣ ባሪያ እንደ ገጸ በረከት እያደረገ በመላክ ያስደስታቸው ነበር ።

ከዚህ በኋላ ከዠርባው የግብፆችንና የዓረቦችን ድጋፍ በማግኘቱ ይልቁንም በእጁ የያዘው አዳዲስ መሣሪያ ሙሉ ልብ ስለሰጠው ወደ ላይ ወደ ይፋትና ወደ ፈጠጋር (የዛሬው ቡልጋና ምንጃር አካባቢው) ሐረርጌዎችንና አዳሎቹን እየላከ ብዙ ሕዝብ አስጨርሶ ብዙ ቤትና አብያተ ክርስቲያናትንም አቃጥሎ ብዙ ከብትም አዘረፈ ። የዚህም ወሬ በቤተ መንግሥቱ ተሰማ ። በዚህም ጊዜ (፲፭፻፰ ዓ. ም.) በተወለዱ በ፲፩ ዓመታቸው የነገሡት አፄ ልብነ ድንግል ዕድሜያቸው ወደ ፳ ዓመት ስለተጠጋ የጦር ሠራዊት ለመምራት አቅማቸው ስለሚፈቅድ ጦራቸውን አስከትተው ወደ ይፋት ጉዞ ዠመሩ ። ማኅፉዝም በባላባታቸው በሡልጣን

(1) በይፋት ውስጥ ደብረ ሲና አጠገብ ማፉድ የሚባለው ከተማና የወረዳ ግዛት በዚህ በማኅፉድ ስም ጥንት የተሠየመው እስከ ዛሬ ስሙን እንደያዘ ማፉድ ገበያ እየተባለ እስከጊዜያችን ድርሷል ። በዓረብኛ ኤሚር (ወይም ይማም) ማኅፉዝ ሲባል ባማርኛ ማኅፉድ ወይም ማፉድ ይባላል ።

መሐመድ ኢብን አዝሃር ኡዲን የሚመሩትን የአዳሎችን ጦር ሰብስቦ መጋቢት በሐምሌ ወር ፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ተሰላለፉ ። መሐመድ ኢብን አዝሃር ከላይ ከወላስሞቹ ዘር የወረደ ለአዳሎቹ እንደ ደንበኛ ንጉሥ የሚቆጠር ነው ።

ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ጦርነቱ በተደረገ በአራተኛው ዓመት ወደፊት እንደ ምናነበው ከዶም ሮድሪግ ጋር ወደ አፄ ልብነ ድንግል ዘንድ የመጣ ጊዜ ከሮድሮ ዳኮቪልሓአና ከየሹማምንቱ እየሰማ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ስለጦርነቱ እንደዚህ ሲል ያትታል «የቤተ መንግሥቱ ሰዎች እየዘፈኑ ስሙን የሚያነሡት (የሚፎክሩበት) ማኅፉዝ የተባለ የእስላሞች አዛዥ . . . ዓቢይ ጾም የሕዝቡን ኃይል እንደሚቀንሰው ስለሚያውቅ ፳፭ ዓመት ሙሉ የንጉሡ ነገሥቱን ግዛት በጾም ወራት ይወር ነበር . . . . ወረራውን ካዛ እስኪንድር ገርምር ባዱ ናዖደም ጊዜ አላቋረጠም . . . በ፳፱ኛው ዓመት (፲፭፻፲፯ ዓ. ም.) በፈጠጋር አውራጃ የገባ ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ ሸሽቶ በየተራራው ሲደበቅ ማኅፉዝ ሕዝቡን እየተከታተለ በየተራሮቹ ላይ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አቃጠለ . . በዚህ መካከል ገበሬውንና ጨዋ የሚባለውን ማርኮ ገበሬውን ለሚመጣው ዓመት ስመለስ ለፈረሶቹና ለሠራዊቱ የሚሆን ብዙ እህል አምርቱ ብሎ አሰናበተው ። ወታደሩን ግን እናንተ የንጉሣችሁን እንጀራ የምትበሉ ነገር ግን አገሩን በደንብ የማትጠብቁ ወስላቶች ብሎ ከመካከላቸው ፲፭፻ ገደለ . . . . . ።

ISIC

ስለዚህ ንጉሡ ነገሥቱ የዚህን ወሬ በመስማት አዝኖ ወደ ጦርነቱ ሊሄድ ወሰነ . . . . . ያገሩ የጦር አለቆች ቢትወደዶቹ ይቢቀሉ አንተ አትሂድ ብለው የመከሩትንም አልሰማም . . . . ወሬው እንዳይሰማ በሩቅ አገር ያለውን ሠራዊቱን ሳይሰበስብ ሌትና ቀን ገሥግሦ ከአዳል አውራጃ በጢት ደረሰና ድንኳኑን አስተከለ . . . . . ሲነጋ ቀይ ድንኳን የተተከለበትን ሠፈር ማኅፉዝ ሲያይ "እኔ እዚሁ ንጉሥ (ለሱልጣን መሐመድ) ስለነገረው ሱልጣኑ አመለጠ . . . . . ለመሞት ቆርጫለሁ አንተ ግን በፈረስ አምልጥ" ብሎ እጠገቡ ላለው ለአዳሉ ጉሡ ነገሥቱን ጦር መንቀሳቀስ እስላሞቹ ባዩ ጊዜ መሪያቸው ማኅፉዝ ከሰልፉ ውስጥ ወጣ ብሎ "ከመካከላችሁ ከኔ ጋር ለመዋጋት የሚደፍር እንዳለ ይምጣ" ብሎ ጠየቀ ። ከዚያ በኋላ የን

በዚያን ጊዜ አባ ገብረ እንድርያስ የተባለ መነኩሴ ተንደርድሮ ሄዶ የማኅፉዝን አንገት በጐራዴ ቀላው . . . ይህ መነኩሴ እስካሁን ድረስ በቤተ መንግሥቱ የሚገኝ በጣም የተከበረ ሰው ነው . . . ወዲያው ክርስቲያኖቹ ተገልብጠው ከእስላሞቹ ጋር ተደባለቁና ውጊያው ተፋፋመ ። እስላሞቹም ተሸነፉ . . . ከዚህ በኋላ ንጉሡ ነገሥቱ በራሱ ከተማ አንድ ቀን እንዳረፈ ወደ አዳሎቹ ባላባት ቤተ መንግሥት ቀርቦ እንደተዘጋ ስላገኘው እንዳይዘረፍ ማንም ሰው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከለከለ . . . .» ሲል ሌላም ዝርዝር ነገር እየጨመረ እዚህ ላይ ያጨርሳል (1) ።

(1) Verdadeira informacao .... የሚባለው የአልቫሬዝ መጽሐፍ በነአቶ ገርማ ትርጉም ምዕራፍ 114



ሎፖ ሶአሬዝ ፫ኛው የሕንድ ገዥ (ከኳሜረር መጽሐፍ)

በዚህ መካከል የሚገርመው በመልእክት ተላልከውና ተስማምተው ይሁን ወይም እንደ አጋጣሚ ይሁን አይታወቅም በዚሁ ዓ.ም. ልብነ ድንግል ማኅፉዝን ወግተው ባሸነፉበት ቀን የሕንዱ የፖርቱጋል አገረ ገዥ ሎፖ ሶዋርስ (LOPO - SOARES) በመርከብ ድንገት መጥቶ ማኅፉዝ ከማይ ካሉት ዓረቦች ጋር ሸቀጥና መሣሪያ የሚለዋወጡበትን የዘይላን የወደብ ከተማ አቃጥሎ አፈራርሶ ተመለሰ ። ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ራሱ በዚህ ጊዜ በመርከብ ከሎፖ ጋር እንደነበረ በመጽሐፉ ጠቅሶታል ። በመጽሐፉ ውስጥ አብዛኛውን ራሱ እያየ የቀረውንም በወሬ እየሰማ የጻፈው በመሆኑ አልቫሬጽ የሚጽፈው አብዛኛው እውነትና መሠረት የያዘ ነው ። አልፎ አልፎ ጥቃቅን ስሕተት በጽሑፉ ጣልቃ ቢገኝም አያስደንቅም ። ለምሳሌ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ከማኅፉዝ ሲዋጉ ዕድሜያቸው ፲፯ ዓመት ነበር ያለው ትክክለኛ ሊሆን አይችልም ። በማንም መጽሐፍ ዘንድ እንደታወቀው የነገሡት በ፲፭፻፰ ዓ. ም. (፲፭፻፹ እ.ኤ.) በተወለዱ ባሥራ አንድ ዓመታቸው ስለሆነ ጦርነቱ የተደረገው በ፲፭፻፰ (፲፭፻፲፮ ዓ. ም.) ሲሆን የግድ በጦርነቱ ጊዜ የሃያ ዓመት የቀረው ቢቀር የ፲፱ ዓመት ወጣት መሆን አለባቸው ።

የሆነ ሆኖ ማኅፉዝ ሞቶ ሡልጣን መሐመድም ሸሽቶ እስላሞቹ ከተሸነፉ በኋላ የክርስቲያኑ ጦር እስከ አዳሎቹ ከተማ እስከ ዘከራ ደርሶ የማኅፉዝን ከተማ አቃጥሎ ያገኘውን ከብትና ገንዘብ ዘርፎ ሠራዊቱ በደስታ ንጉሠ ነገሥቱን አጅበው ወደ ሥፍራው ተመለሰ ። ከዚህ 1516 ዠምሮ የወጣቱን ንጉሠ ነገሥትና የመንበረ ቤተ መንግሥቱም ሕዝቡም ማድነቅና ማሞገስ ዠመረ ።

የማኅፉዝ ገዳይ አባ ገብረ እንድርያስ ካዜ በዕደ ማርያም ዠምሮ ከሹመት ወደ ሹመት እየተዛወሩ እስከ አፄ ልብነ ድንግል የደረሱ የቤተ መንግሥትና የቤተ ተናጋሪና ዘላፊም ይመስላሉ ። የንግግሩን ዓይነት ሳይገልጽ የአልቫሬጽ መጽሐፍ ባዔ ናዖድ ዘመን መላሳቸው ተቆርጦ እንደነበረ በዚሁ ምዕራፍ ፻፲፬ ላይ እንደዚህ ሲል ይገልጻል «አባ ገብረ እንድርያስ በጣም የተከበረና ብዙ ገቢ ያለው መነኩሴ ነው ። ከዚህ የጀብዱ ሥራ (ማኅፉዝን ከመግደላቸው) በቀር ብዙ ታላላቅ ጀግንነት በሌላ ጊዜ ሠርቷል . . . . . ንግግርም አዋቂ . . . . . . ፖርቱጊዞችን የሚወድ ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚረዳ ነው . . . . . ይህ ሰው በጣም ማውራት ስለሚወድ ዓፄ ናዖድ መላሱን አስቀንጠበው ይባላል ።»

እኚሁ አባ ገብረ እንድርያስ እስከ ግራኝ አህመድ መነሣት ቆይተው በመጨረሻ ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር ሆነው ከግራኝ አህመድ ጦር ጋር ሲዋጉ ተማርከው ሞቱ ። ወደፊት ከሥፍራው ስንደርስ እንደምናነበው ይኸንኑ አሟሟታቸውን ሲተርክ ሙሴ ረኔ ባሴት ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ እንደዚህ ይላል ‘‘ወሰን ሰገድ የተሸነፈለት ከአድማስ ንጉሥ (በዕደ ማርያም) ዠምሮ በኢትዮጵያ ያልገዛሁት አገር የለም እያለ የሚፎክረው ገብረ እንድርያስ ሞተ ።

ሊሞትም ዕድሜው ዘጠና ነበር” (1) ።

እኝህን ሰው መጽሐፉ አባ ገብረ እንድርያስ ስለሚላቸው መነኰሴነታቸውን ያስረዳል ። ነገር ግን የዚያን ዘመን አብዛኛው ከፍተኛው ባለሥልጣን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ተግባር በድርብ የሚፈጽም ሆኖ ይገኛል ። ወይም አባ ገብረ እንድርያስ በመገርመሪያው ዘመናቸው የታወቁ ተዋጊ የጦር መኰንንና አገረ ገዥ ሆነው ሲኖሩ ወደ ዘመናቸው መጨረሻ እንደተለመደው መንኵሰው ስለነበረ ጸሐፉ ስማቸውን የሚያነሣው ከመነኰሱ በኋላ ይሆናል ። በዚህም ዓይነት የሽማግሌና የመነኰሴ ጐበዝ ኖረዋል ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ይህ የማኅፉዝ ጦርነት ከተደረገበት ከ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ዠምሮ ግራኝ አህመድ እስከተነሣበት ጊዜ እስከ ፲፭፻፴፭ - ፴፮ ዓ. ም. ድረስ አሥር ዓመት ምንም እንኳን አንዳንድ ጥቃቅን ሽፍትነት ባይጠፋ በጠቅላላው ግን ባገር ላይ ሙሉ ሰላምና ፀጥታ ሆኖ ተድላና ደስታም በርክቶ ሽፍታና ሌባም ጠፍቶ እርሻና ንግድ በዚያው በመጠኑ ተስፋፍቶ ነበር ይባላል ። ንጉሡም ዕድሜያቸው ሃያ ዓመት ስላለፈ ሞግዚቶች የነበሩት ያያታቸው ባለቤት ንግሥት እሌኒና እናታቸው ናዖድ ሞገሳ ቀርተው በቀጥታ ንጉሣዊ ሥልጣናቸውን ይዘው በሙሉ ያስተዳድሩ ዠመር ። በፍርዳቸውም ሰውን ሁሉ አስደሰቱት ከችሎትና ከሌላውም የተረፈውን ጊዜያቸውን ከሊቃውንቱና ከዓቃቤ ሰዓቱ (ነገደ ኢየሱስ) ጋር በመነጋገር ያሳልፉ ዠመር ።

ISIC

በዚህ መካከል ልናስታውሰው የሚገባን በዚህ ሰዓት የቱርክ ሱልጣን ሰሊም ከዚህ በፊት ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው በዚሁ ኤሚር ማኅፉዝ በተሸነፈበት ዓመት እ.አው.ቀ. በ፲፭፻፲፮ ዓ.ም. የማብፅን ጦር አሌፕ (ሶርያ) ላይ ከማሸነፈበት ብፅ ሱልጣን ከአልጋውሪ ጋር ተዋግቶ ያሸነፈበትና ሶርያን ፓለስቲንን የወረረበት በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ራሱን ግብፅን ወርሮ የመጨረሻውን ሱልጣን ቱማንን ካስማረከ በኋላ አታሎ በግፍ የሰቀለበት ጊዜ ስለሆነ እዚያው በከፍተኛ ደረጃ ጦርነት ቱርክ ግብፅን ያስጨነቀበት ግብፆችም ዓረቦችም ወደዚያው ወደ ቱርክ አሳባቸው ስለተሰቀለ ወደ ኢትዮጵያ ፊታቸውን መልሰው የማኅፉዝን ደም ለመበቀል ወይም የሸሸውን ሱልጣን መሐመድን እንደገና ቀስቅሰው ለማዋጋት ጊዜ አላገኙምና ሁኔታው ላዌ ልብነ ድንግል ለመገርመሪያ የግዛታቸው ጊዜ የተመቸ ነበር ለማለት ይቻላል ።

ዳሩ ግን የቱርኮቹ ፤ የዓረቦቹ ፤ የግብፆቹ ርዳታ ለማኅፉዝ ጊዜ የሳተው በሚቀጥለው ጊዜ እሸናፊዎቹ ቱርኮችና ተሸናፊዎቹ ግብፆች ከዓረቦቹ ጋር በእስላምነት ተባብረው ለግራኝ አህመድ ተፈጸሞ ባዌ ልብነ ድንግል መጨረሻ ዘመነ መንግሥት በተድላና በደስታው ፈንታ የጦርነትና የመከራ ዘመን ሲተካ ወደፊት በዝርዝር እንመለከታለን ።

እንግዲህ በማኅፉዝ ላይ በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ይህ ያገኙት ድል አድራጊነት ላዌ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 260 - 267

ልብን ድንግል የመዠመሪያውም የመጨረሻውም ነው ማለት ነው ። ይህ ድል ፲ ዓመት ያህል የሰላም ጊዜ በመስጠት አዘንግቶ ከአቶየ በኋላ በሰላሙ ጊዜ ሠራዊ ውን ሳያደረጁ አዳዲስ ዘመናዊ መሣሪያ ሳይሰበስቡ የግራኝ አህመድ ወረራ እንደ ቀጠር በዕድል በርሳቸው ጊዜ ደርሶ አገራቱን የመከራና የነግር ጉርፍ አጥለቀለ ቀት ። መሣሪያ ለመሰብሰብ ጦር ለማጠንከር የነበራቸው የተመቸና የሰላም ጊዜ ይኸው አሥሩ ዓመት ነበር ። ይኸንንም ሊያገኙ ይችሉ የነበሩት የገዥዎቹና እጅ ከዘረጋላቸው ከፖርቱጋል መንግሥት ነበር ። ዳሩ ግን ይኸን የተንጠለጠለ የጦር ደመና ሳይጠረጥሩ በዚህ ጊዜና በዚህ መንግሥት ሳይጠቀሙ ባለፈ ድል በቆየ ታሪክ ባለው መሣሪያና በሠራዊታቸው ብዛት ብቻ ተማምነው ስለተቀመጡ ከዚሁ ከወዳጅ አገር ከፖርቱጋል የመጡትን መልክተኞች በደንብ ተቀብለው ለመነጋገር ብዙ ቀን ደጅ አስጠንተው ባገራቸው ፮ ዓመታት አቆይተው ሰደዱዋቸው ። ከጦር ነቱ ቀደም አድርገን የእንግዶቹን አመጣጥና የአቀባበሉን ሁኔታን በሚቀጥለው እንመልከት ።

ምዕራፍ ፲፯

የፖርቱጋል መልክተኞችና የሕንድ ገዥ ምጥዋ መድረስ (፲፭፻፲፪ ዓ. ም.) ።

ISIC

በምዕራፍ ፲፩ እንደተጻፈው ከንግሥት እሌኒ የተላከው አርመኑ ማቴዎስ ሊስቦን ከገባ ዠምሮ ወደ ሮማ እስኪሄድ ድረስ እንደ እንደ መስፍን በጌትነትና በክብረት ተቀምጦ የኢትዮጵያን ሀብታምነት የሕዝቡንም ገዢነት በየጊዜው ለንጉሡ ለአ ማኑኤልና ለአካባቢው ሲተርክ ሰነበተ (1) ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ከአክሱም ውድቀት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግ ሥት ከውጭ መንግሥት ግንኙነቱን አቋርጦ ከ፰ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ከሰሜን ከአክሱም ወደ መካከል ወደ ላስታ ከዚያ ደግሞ ከ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ የባሰ ውን ርቆ በሸዋ ውስጥ ሆኖ ንግሥት እሌኒ በደብዳቤአቸው እንዳሉት ከወደብ ከባ ሕር ርቆ ስለተቀመጠ ስሙና ዝናው ለአውሮፖች ተሰውሮባቸው የሌለውን በመ ላና በስሕተት የንጉሡን ስም ቄስ ዮሐንስ ፡ አገሩንም ኢትዮጵያ ወይም ሐበሻ በማ ለት ፈንታ ሕንድ እያሉ በመጥራት ፡ ክርስቲያንነቱን ብቻ እንጂ በትክክልም ያለ በት ሥፍራ ኃይሉና ድርጅቱም እስከምን ያህል ድረስ መሆኑን ከለማወቅ የተነሣ ከንጉሥ አማኑኤል በፊት የነበረው የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፪ኛ በነገሠበት ጊዜ (፲፬፻፸፫ - ፲፬፻፹፯ ዓ. ም.) ሄዳችሁ ይኸ ክርስቲያናዊ አገርና የክርስቲያን ንጉሥ የሚገኝበትን ቦታ ፈልጋችሁ አግኙና ተመልሳችሁ ንገሩኝ ብሎ ፔድሮ ደ ኮቪልሐአንና ጓደኛውን አልፍንሶ ደ ፓይቫን ከላከ ወዲህ ደ ኮቪልሐአ ብቻውን

(1) Viagens de Pedro da Covilhan ምዕ. VII ገጽ 206-208

ባዬ እስክንድር ጊዜ (፲፬፻፸፰ - ፲፬፻፺፩ ዓ. ም.) ደርሶ አሁንም በኢትዮጵያ ባዬ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት ይገኛል ። ከመጣም ፴ ዓመት ስለሆነው ያገሪቱን የቤተ መንግሥቱን ልማድና ቋንቋ ደህና አድርጎ ስለሚያውቅ ባሁኑ ጊዜ ካገሩ የመጡትን እንግዶች በማናቸውም ሲረዳ ወደፊት እንመለከታለን ።

ስለዚህ ለማወቅና ለመዛመድ የናፈቁትን የክርስቲያን አገር መላክተኛውን ራሱን ብዙ ተስፋ ከሚሰጥ ደብዳቤ ጋር ሲያገኙት የፖርቱጋል ንጉሥና ሹማምንቱ ማቴዎስን እንከባከበው መያዛቸው ፤ የሚለውንም በናፍቆት ማዳመጣቸው የታወቀ ነው ።

የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል በዘመኑ ከሰፊው ግዛቱ ከሕንድ ጋር በመካከለኛ ምሥራቅ የሚገኙትን አገሮች ለመደባለቅ ኢየሩሳሌምንም ከቱርክ ግዛት ለማውጣት ምኞት ስለነበረው በጉዳዩ ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ጋር አሳብ ለአሳብ ይለዋወጥ ነበር ። ነገር ግን ከሦስት መቶ ዓመት በፊት እ. አው. ቍ. ከ፩ሺ፺፮ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ ፲፪፻፺፩ ዓ. ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ለአውሮፓ ነገሥታት ለነሪቻርድ ከር ደልዮን (የአንበሳ ልብ) ለነፍሬድሪክ ባርባሩስ (ባለቀዩ ጢም) ካረቦች ለማስለቀቅ የመስቀል ጦርነት በሚባለው ጊዜ በኅብረት ያጋግመው ተዋግተው ያልሆነው አሁን ፖርቱጋል ብቻውን ኃያሉን የቱርክ መንግሥት ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት እንደማይሆንለት የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ፲፩፻ው ጊዜ በግብፅ ባለሥልጣኖች ሥር የሚገኙት የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት በዚህ ጊዜ የመንፈሳዊ አባትነታቸው ሥልጣን ስለተዳከመ ከመንፈሳዊ ልጆቻቸው ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋር ግንኙነታቸው እየተቋረጠ ብዙ ዘመን ስለቆየ የኢትዮጵያን ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከነበረችበት ከመንበረ ማርቆስና ከእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት ሥር አውጥቶ ወደ ካቶሊካዊት መንበረ ጴጥሮስ ወደሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሥልጣን ሥር ለማዛወር ተስፋ በማድረግ ንጉሡ አማኑኤልና የሮማው ሊቀ ጳጳስ ሳይጸጸፉበት አልቀሩም ።

በዚህ ምክንያት አሁንም የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል ደብዳቤ አሲዞ ወደ ሮማ ሊቀ ጳጳስ ወደልዮን ፲ኛ (፲፭፻፲፫ - ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) ማቴዎስን ላከው ። ንጉሡና ሊቀ ጳጳሱም በመልእክት ተስማምተው ከቤተ ክህነት ወገን የካቶሊክን ሃይማኖት ለመስበክ ጭምር በመጽሐፉ ምክንያት ባለፈው ብዙ ጊዜ የጠቀስነው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ (Francesco Alvarez) ጂዎቫኒ ፌርናንዴዝ (Giovani Fernandez) ፒየትሮ አልፎንሱ ሜንዴዝ (PIETRO ALPHONSU MENDEZ) ከቤተ መንግሥት ወገን የፖለቲካውን ወገን የሚመራ ዶም ኤድዋርድ ጋልቫም (DOM EDUARDO GALVAM) ሌሎች ተከታዮች ተጨምረው ከማቴዎስ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተመረጡ ። እነሱም ከፖርቱጋል ንጉሥና ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ለእቴጌ እሌኒና ለወጣቱ ንጉሥ ለአጼ ልብነ ድንግል የሚሰጥ ደብዳቤና ገጸ በረከት ይዘው እ.አው.ቍ. ጥቅምት ፩ ቀን ፲፭፻፲፬ ዓ.ም. ግድም በመርከብ ተሳፈሩ ። ተጉዘውም ካማራን እሚባለው ወደ የመን ግዛት ከሚጠጋው የቀይ ባሕር ደሴት ሲደርሱ የመልክተኞቹ አለቃ ጋልቫም ከመንገድ ጉዞ ጋር በቀይ ባሕር ዳር



ዲዬጐ ሎፔዝ (ከካሜሬር መጽሐፍ ላይ የተገኘ)

የሚሰማው የበረሃ ሙቀት ስላደከመው በዕድሜም የሸመገለ ነበረና ሞተ ። ከመካ ከላቸው ሦስቱ ጳሕላት ደሴት ከደረሱ በኋላ ሞቱ ። የተረፉትም ተስፋ በመቁረጥ ወደ ኢትዮጵያ ጉዟቸውን መቀጠላቸውን ትተው ግዛታቸው ወደ ሆነው ወደ ሕንድ ሄዱ ። በዚያም ሳሉ ከሎፓ ሱአሬዝ በኋላ ዲዩጎ ሎፔዝ(DIEGO LOPES) የሚባለው በሕንድ የፖርቱጋል አገረ ገዥ እንደገና ወታደር ያለበት አዲስ መርከብ አዘጋጅቶ መላክተኞቹን በዚያ አሳፍሮ በየመንገዱ የሚገጥመውን የቱርክ ወታደር እየመታ አልፎ ከኅአ በተነሡ በሁለተኛው ወር በሚያዝያ ፲ ቀን ፲፭፻፳ ዓ.ም. እ. አ. ቆ. ምጥዋ አጠገብ ደረሰ ።

የእያራረሳቸውን ሁኔታ የአልቫሬጽ መጽሐፍና ከካስታንሔድ መጽሐፍ ከፖርቱጋልኛ ወደ ፈረንሣዊኛ የተተረጎመው እንደዚህ ይላል (1) «. . . . . . በዚያን ሰዓት ምጥዋ ሁለት ትልልቅ ብዙ ትናንሽ የሞር (ዓረቦች) መርከቦች ነበሩ ። የኛን መርከቦች መምጣት ሲያዩ መልሕቃቸውን ነቅለው ሸሽታቸውን ዠመሩ ። ዠሮኒሞ ደ ሱዛ ( Jeronimo de sousa ) የሚባለው የኛ ካፒቴን (ሻምበል) ሁለቱን መርከቦች እያባረረ ደርሶ አንዱን አቃጠለው ። ከዚያ ትናንሾቹን መርከቦች እያሳደደ አርኪቆ ከሚባለው መንደር ደረሰ . . . ፖርቱጋሎቹም የመንደሩን ቤት ከመርከባቸው ላይ ሆነው ሲመለከቱ . . . ሦስት ሰዎች ከመንደሩ በታንኳ ተሣፍረው መጡ ። ወደ መርከባችንም ወጡና ምንድናችሁ ብለው በዓረብኛ ጠየቁ ። የኛዎቹም የፖርቱጋል ንጉሥ ሎሌዎችና ክርስቲያኖች ነን ቢሏቸው ISIC ሲሉ የካፒቴኑን እግር ስመው በደስታ እንዲህ አሉ "ክርስቲያኖች ! ! ! ክርስቲያኖች ! ! ! ኢየሱስ ክርስቶስ የቅድስት ማርያም ልጅ . . . . . ." ። አንዱ ከመርከቡ ወርዶ ለአርኪቆ ካፒቴን (ሹም) ወሬውን ሊነግር ሄደ ። ከቀሩት አንዱ አበሻ ክርስቲያን አንደኛው ሞር (እስላም) ነው ። እነርሱንም ወደ አገረ ገዥው ዘንድ አመጡና አገናኙዋቸው . . . እርሱም ማን መሆናቸውን ሲያውቅ በደስታ ተቀበላቸው ። አበሻውም ከአርኪቆ ሹም የተላከ ደብዳቤና እንድ ለሰላም ምልክት የሚሆን የብር ቀለበት ላገረ ገዥው ሰጠ . . . ደብዳቤው . . . . "ክርስቲያኖቹ አንድ ቀን በምጥዋ ይገባሉ እየተባለ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ ይተነበይ የነበረውና አበሾቹ ይጠባበቁት የነበረው ትንቢት ስለደረሰ አምላኩን ያመሰግናል . . . . . የፖርቱጋሉ ገዥ የባሕር ጌታ ስለሆነ መሬቱንም እንደፈቃዱ እንዲያዝበት . . . . . . እርሱም የአርኪቆ ሹም በክርስቲያኖቹ እምነት ሰላለው መንደሩን ትቶ ከነሕዝቡ አልሸሸምና አገረ ገዥው (የፖርቱጋሉ) የሰላም ምልክት እንዲልክለት ይጠባበቃል" የሚል ነው ።

ይህ ደብዳቤ በተነበበ ጊዜ እዚያ ከነበሩት ብዙዎቹ ተረስቶ የነበረውን ይህን የክርስቲያን አገር በማሰብ በደስታ አለቀሱ ። ከዚህ በኋላ አገረ ገዥው ለመላክተኞቹ ጥሩ ጥሩ ልብስ ከሸለማቸው በኋላ አንድ ነጭ ባንዲራና ቀይ መስቀል የሰላም ምልክት እንዲሆነው ለአርኪቆው ሹም ያስረከቡት ዘንድ ሰጣቸው ። እንደዚሁም

(1) Verdadeira..... ምዕ. 1-4 ። Viagens De Covilhan ምዕ. VII ። Castanheda በገጽ 132 - 134

ለጸፈለት መልስ የሚሆን ደብዳቤ እሲዞ መልክተኞቹን በጀልባ መልሶ ላካቸው ። እነርሱም በጀልባቸው ተሳፍረው መሄድ ሲጀምሩ ባገረ ገዥው ትእዛዝ ስለደስታ የጥይት ሮምታ ባንድ ጊዜ ተተኮሰ ። ጀልባው ወደ መሬት ሲጠጋ ከመላክተኞቹ አንዱ ዓረብ (ወይም እስላም) ወሬውን ቀድሞ ለመንገር ሲል ከጀልባው ወርዶ እየዋኘ ሄደ ። ወሬው ሲሰማ በአርኪቆ ሰፈር ደስታ ሆኖ ክርስቲያኑም እስላሙም ሁለት ሺህ የሚሆን ሕዝብ እየሮጠ ወደ ባሕሩ ጠረፍ መጣ ። ጀልባው ወደ ጠረፍ ሲጠጋ ሰው ሁሉ እየተጯጯኸ በመንተት ወደ የብስ አመጡት ።

በዚያን ጊዜ ሸሙ መጥቶ ካገረ ገዥው የተላከውን ሰንደቅ ዓላማ በክበሬታ ተቀብሎ መላክተኞቹን በደንብ አስተናግዶ ሰንደቅ ዓላማው ከቤት በላይ ተሰቀለ ። አገረ ገዥው በጻፈለት ደብዳቤ ውስጥ እርሱንና (የአርኪቆ ሽም) ከደብረ ቢዘን መነኮሳትም ውስጥ ለመገናኘት ፍላጎት እንደነበረው በደብዳቤ አስታወቀ ። ይህም አገረ ገዥ (ባሕር ነጋሽ ?) ግዛቱ ከአርኪቆ ጀምሮ እስከ ሱአኪም ይደርሳል . . . . እርሱም ለቄሱ ዮሐንስ (ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት) ገባር ስለሆነ ሁልጊዜ ከጎረ ቤት ከእስላሞቹ ንጉሥ ጋር እንደተዋጋ ነው ።

በመካከሉ የፖርቱጋል አገረ ገዥ የምጥዋን ደሴት (ወደብ ማለቱ ይሆናል) ለመጎብኘት ሄደ ። በዚያም ጥሩ ውኃ በማጠራቀሚያ ውስጥ እንዳለ ነግረውት ነበር . . . ምጥዋንም በጎበኘበት ሰዓት አንድ ትልቅ ምሽግ የሚሠራበትን ሁኔታ ሲአጠና ደህና ሰፊ ወደብ እንደ[illegible]ም ተገነዘበ . . . . . . ቢያስለኳውም አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብራስ ሆነ . . . . . . (1) ።

ከዚህ በኋላ የፖርቱጋሉ አገረ ገዥና የሐበሻው አገረ ገዥ (ባሕር ነጋሽ) በደጁ ተገናኝተው ውላቸውን በመሐላ ፈጸሙ ። ቄሱ (የኢትዮጵያ ንጉሥ) ፖርቱጋሎቹ ከእስላሞቹ ጋር ሲዋጉ ሙሉ ርዳታውን ለፖርቱጋሎቹ እንዲያደርግ ። ፖርቱጋሎቹ እስላሞቹን ከዳሕላቅና ከምጥዋ እንዲያስወጡ ቄሱ በራሱ ወጭና ኪሣራ በነዚህ ሥፍራዎች ምሽግ እንዲያሠራ ። በምሽጉ ግን የፖርቱጋል ወታደሮች ተቀምጠው እንዲከላከሉበት ።

ይህ ወዳጅነት (ውል) በታላቅ ደስታና በመሐላ ተፈጸመ ። ሁለቱም አገረ ገዥዎች በብዙ ሰው ታጅበው ሌላ ብዙ ነገር ሲጫወቱ ከቆዩ በኋላ የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ ለአበሻው አገረ ገዥ በጥሩ ዓይነት የተሠራ ሁለት ጥሩር (ብረትማ ልብስ) ፤ አንድ ሙሉ የከርቻ ዕቃ ፤ ሰይፎች ፤ ጋሻዎች ፤ ሳንጃዎች ፤ ሁለት ከሐር የተሠሩ ካባዎችና ሌሎችም ዋጋቸው የከበረ ዕቃዎች ሰጠው ።

ሁለቱ አገረ ገዥዎች ተሰነባብተው የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ ወደ ታንኳው ሲገባ ፤ ለአክብሮት ሲል ታንኳው እስኪሄድ ድረስ ባሕር ነጋሹ በዚያው ቆሞ ይጠብቅ ነበር እንጂ አልሄደም ። ከዚያ በኋላ ባሕር ነጋሹ ወደ አርኪቆ ሄደ በዚያው ቀን ለፖርቱጋሉ አገረ ገዥ አንድ ፈረስ ፤ አንድ በቅሎ ፤ ሃምሳ የተንደ ከብት . . . . . ላከለት . . . . . .»

(1) አንዱ ብራስ የሁለት ሰው የተዘረጉ ግንዶች ያህል የሚረዝም ነው ።

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ጽሑፍ ከዚህ በፊት እንደተመለከተው ቀድሞ ርናየ ሎፔዝ ደ ካስታንሄዳ በፖርቱጋል ቋንቋ በዝርዝር ከጻፈው በሕንድ የድል ግድረግ ታሪክ ከሚባለው ውስጥ ፍሬፍሬውን ለቅሞ የፖርቱጋሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደፈረንሣዊኛ ተርጉሞ በ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. ካሳተመው መጽሐፍ ላይ ተገኘ ነው (1) ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የአርኪቆው ሹም ወደ ፖርቱጋሉ አገረ ገዥ በጻፈው ደብ ዳቤ ላይ ክርስቲያኖች ምጥዋ ይገባሉ ይኸውም ማለት ከእስላሞቹ እጅ አውጥ ተው ይይዙታል የሚባለው ትንቢት በመድረሱ እምላኩን ያመሰናግል ያለው ከዚህ በፊት ንግሥት እሌኒ ለአማኑኤል ንጉሥ በጻፉት ደብዳቤ ላይ "በፈረንጅ አገር አንድ ንጉሥ ተወልዶ እስላሞቹንና አረመኔዎቹን ያጠፋቸዋል የሚባለው ትንቢት እነሆ ደረሰ" ካሉት ጋር የሚገጥም ነው (2) ።

ይሁን እንጂ ትንቢቱ በፍጹም አልተፈጸመም ወደፊት በሚመጣው ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳን በኋላ ተመልሶ ቢቋቋም እንዲያውም የገላቢጦሽ የክርስቲ ያኑ ያኤ ልብነ ድንግል መንግሥት በእስላሙ በግራኝ አህመድ ወረራ ተደመሰሰ ። የቱርክ መንግሥትም ገናንነቱን እንደያዘ ከዚያን ጊዜ ዠምሮ (፲፭፻፲ ዓ. ም.) እስከመዠመሪያው ትልቁ ጦርነት ፍጻሜ ድረስ (፲፱፻፲፱) ዓ. ም. ድረስ አራት መቶ ዓመት ሙሉ በገናንነት ኖረ ። ከዚያም ወዲህ የሰው አገር መግዛት ቀረበት እንጂ በስመ ጥሩው መሪ በአታቱርክ ተቋቁሞ የራሱን አገር እስከዛሬ እንደያዘ ይቀጥላል ። ግብፆችና ሌሎችም የዓረቦቹ አገሮች ያሉበት ሁኔታ የታወቀ ነው ።

በመርከብ ምጥዋ ድረስ ለመጣው ለዚህ ለፖርቱጋል አገረ ገዥ ደብዳቤና መላክተኞች የላከው ይህ የአርኪቆ ሹም የፖርቱጋሎቹ ጽሑፍ ካፒቴን የሚለው የኛና ያረቦቹ ጽሑፍ የሹመት ስሙን ናይብ ይለዋል ፣ ትርጓሜው ምስለኔ ማለት ነው ። ይኸም ባላባት ዘሩ ዓረብም ኢትዮጵያዊም ቢሆንም ሃይማኖቱ እስላም ነው ። እርሱና እርሱን የመሰሉት የሱአኪም የዳሕላቅ የምጥዋ ባላባቶች ምንም እንኳ ሃይማኖታቸው እስላም ቢሆን ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ጊዜና ኃይል ለሰጠው የሚገዙ ስለሆነ ቱርኮቹ ሲያይሉ ለነርሱ ሲገብሩ እነርሱንም ሲያስተና ብሩ መቆየታቸው የታወቀ ነው ። እንደዚሁም የኢትዮጵያ ነገሥታትና የዚያ አው ራጃ ገዥዎቻቸው ባሕር ነጋሾች ሲጠነክሩ በነርሱ ውስጥ እየታዘዘና ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እየገበሩ ሰላማዊ ኑሮአቸውን የሚቀጥሉ ናቸው ። የወደቡን ከተማ የውጭ አገር ጽሑፍ አርቂቆ ሲለው የኛ ጽሑፍ ድሆኖ ይለዋል ።

አሁን ደግሞ የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ ራሱ ዲዩጎ ሎፔዝ ከሕንድ ድረስ ባዲስ አገ ኃይል የጦር መርከብ ይዞ መጥቶ በምጥዋ ያሉትን የቱርክ መርከቦች አባርሮ አገ ሩን ሲይዝ ከዚያም ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ወኪል ከባሕር ነጋሹ ጋር በሚዋዋ ልበት ጊዜ በመዠመሪያ ተገናኝቶ የሰላም መልእክት መለዋወጡና ማስተናገዱ

(1) ምዕራፍ 10 ገጽ 128 - 143 ።

(2) የዚህ ትንቢት መሠረት በገድለ ፊቅጦር መገኘቱን ዓፄ ልብነ ድንግል ወደፊት ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤል በሚጽፉት ደብዳቤ ላይ ይገልጣሉ ።

ISIC

ይኸንኑ ሰላማዊ ተገዥነቱን ለማጽደቅ ነው ። ላገረ ገዥርው በጻፈው ደብዳቤ ላይ ‘‘በክርስቲያኖቹ ላይ እምነት ስላለኝ ሕዝቤን ይገር ከመንደረ አልሸሽሁም’’ ያለው ራሱ የሰላማዊነቱን ምልክት የብር ቀለበት ልኮ ንጉሡ ባንዲራ የተቀበለውም በዚሁ ምክንያት ነው (1) ።

የፖርቱጋሎቹ ጸሐፍ ቢርኤጋግስ እያለ በስሕተት የሚጠራው ባሁኑ ጊዜ ከፖርቱጋሉ አገረ ገዥ ጋር ተገናኝቶ እላይ የተጠቀሰውን ውል የተዋዋለው ፤ ብዙ አሳብና ገጸ በረከት የተለዋወጠው ባሕር ነጋሽ ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ባሕር ነጋሽ ዮሪ ነው ። እርሱም የዓፄ ልብነ ድንግል እናት የእቴጌ ናዖድ ሞገሳ ወንድም ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጸው የሕንድ አገረ ገዥና ባሕር ነጋሹ በተዋዋሉት መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት ወደፊት ባለው ጊዜ ውስጥ በምጥዋ ምሽጉን በራሱ ኪሣራ ሠርቶ ለፖርቱጋሎቹ ማስረከቡን ፖርቱጋሎቹም ምሽጉን ይዘው የምጥዋን ወደብ ለራሳቸው ወይም ለኢትዮጵያ ወይም ለሁለቱ ጥቅም መከላከላቸው የተጻፈ አላየሁም ። ምናልባት ውሉ ከመፈጸሙ በፊት የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ እንአልቫሬጽን ምጥዋ አድርሰ መርከቡን ይዞ ወደ ሕንድ ከተመለሰ በኋላ ቱርኮቹ እንደገና ተዘጋጅተው መጥተው ምጥዋን ወስደውት ይሆናል ። ይኸንንም ለማመን የሚያስገድደን ከሐያ ዓመት በኋላ ግራኝ ኢትዮጵያን በወረረ በ፲፭ኛው ዓመት ፬፻ የፖርቱጋል ወታደISICሮች ኢትዮጵያን ሊረዱ በዚሁ በምጥዋ በኩል ሲመጡ ቱርኮቹን በጦርነት ተዋግተው አሸንፈው አለቃቸውን ኑር ኡድን የሚባለውን ገድለው ማለፋቸው ነው ።

ዲዩን ሎፔዝ መላክተኞቹን ይዞ ምጥዋ በገባበት ዓመት (እ. ኢ. አ. ፲፭፻፴፰ ዓ.ም.) በቀላሉ የምጥዋን ወደብ ለመያዝ የቻለው የአርኪቆና የምጥዋ ሹማምንትም በሰላም የተቀበሉበት ምክንያት በዚህ ዓመት ስመ ጥሩው የቱርክ ሱልጣን መካከለኛውን ምሥራቅና ግብፅን ያስገበረው ሳሊም ሞቶ ልጁ ሰሊማን የነገሠበት ዘመን ስለሆነ ባንድ ወገን ንጉሥ በሚለዋወጥበት ዓመት ሁከትሁከት ስለማይጠፋ ይግሞ በአውሮፓ ከሐንጋሪ ንጉሥና ከጀርመን ንጉሠ ነገሥት ጋር ቱርኮች ግዛት የሚፋለሙበት ጊዜ ስለሆነ በዚህ በሁለቱ ምክንያት ከቀይ ባሕር የባሕር ኃይላቸው ያነሰ ባለበት ሰዓት ይሆናል ።

አዲሱ ሱልጣን ሰሊማን በዙፋኑ ሲረጋገጥ ዲዩን ሎፔዝም ወደ አገሩ ወደ ሕንድ ከተመለሰ በኋላ በተለይ እንሮድሪግ ከኢትዮጵያ ወደ ፖርቱጋል ከተመለሰበት ከ፲፭፻፵፫ ዓ. ም. ወዲያ የቀይ ባሕር በቱርክ መርከቦች ቊጥጥር መመለሱ የታወቀ ነው ። ነገር ግን ግዛት በጣም ሲሰፋ የምድርም የባሕርም ኃይል በያለበት እየተበተነ መከፋፈሉ ግዴታ ስለሆነ አሁንም ወደፊት እንዘረዝር እላይ የጠቀስናቸው ፬፻ የፖርቱጋል ወታደሮች ኢትዮጵያን ሊረዱ ሲመጡ የቱርኮቹ መርከቦች ምንም ቢዋጉ ፈጽመው ሊያግዷቸው አልቻሉም ። ሁኔታውንም በሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ።

(1) የአልቫሬጽ መጽሐፍ ምዕ. 21

## ምዕራፍ ፲፰

## የፖርቱጋል መልእክተኞች ከምጥዋ ወደ ደብረ ሊባኖስ መድረስ - የእጨጌ ዕንባ ቆም ሹመትና ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጐሟቸው መጻሕፍት ።

ባለፈው ምዕራፍ እንደተጻፈው ፖርቱጋሎቹ ምጥዋ በሰነበቱበት ጊዜ ከደብረ
ቢዘን መነኮሳት ጋር መነጋገራቸው ፣ ምጥዋም በነበሩበት ሰዓት በምጥዋ ከተማ የነ
በረውን የእስላሞቹን መስጊድ ውስጡን ለዋውጠው ቤተ ክርስቲያን አድርገው
እንደቀደሱበት ፣ የቤተ ክርስቲያኑም ስም ጽንሰታ ለማርያም ተብሎ እንዲሠየም
የፖርቱጋሉ ሹም ማሰቡ በየመጽሐፉ ተጽፏል (1) ። ጽንሰታ ለማርያም ተብሎ
ይሠየም ማለቱም ወደፊት እየሰፋ የሚሄደው የፖርቱጋልና የኢትዮጵያ ዝምድና
በዚህ ሥፍራና ጊዜ በምጥዋ መጸነሱን ለማስረዳት ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ዋናው ዓላማ ከሊስቦንና ከሮማ የፖርቱጋሉን ንጉሥና የርእሰ
ሊቃነ ጳጳሳቱን መልእክት ለኢትዮጵያ ንጉሥ ላዒ ልብነ ድንግልና ለንግሥት
እሌኒ ለማድረስ የተላኩት መልእክተኞች ከዚህ በፊት ምጥዋ ድረስ መጥተው
መከራ አግኝቷቸው ግማሾቹም በየደሴቱ ሞተው የቀሩትም ይኸንኑ ዋና የንጉሥ
መልእክት ለማድረስ ከመጠባበቅ ላይ ናቸው ። ራሱ የሕንድ አገረ ገዥ የጦር መር
ከብ ይዞ ወደ ምጥዋ የመጣበት ዓይነተኛ ጉዳይ ለመመላለሻ የሚጠቅመውን የም
ጥዋን ወደብ ከቱርኮች እጅ አውጥቶ በነፃ ከያዘ በኋላ እስከዚህ መልክተኞች ወደ
ኢትዮጵያ ለመላክ ሲሆን ወደቡም ለዘለቄታ በኢትዮጵያና በፖርቱጋሎች እጅ
እንዲሆን ነው ።

የንግሥት እሌኒን መልእክት ካሥር ዓመት በፊት ለፖርቱጋል ንጉሥ ለማድ
ረሰ ሄዶ የነበረው የአርመን ተወላጅ ማቴዎስ በአሁኑ ሰዓት ከነዚሁ ከመልክተ
ኞቹ ጋር አብሮ ነበር ። ዳሩ ግን መልክተኞቹን እየመራሁ ወደ ዓፄ ልብነ ድንግል
እሄዳለሁ እያለ ሲመኝ በዚሁ ምጥዋ በሰነበቱበት ሰዓት ታሞ ሰንብቶ ኖሮ ሞተና
በደብረ ቢዘን ተቀበረ (2) ።

እንደዛሬ የአየር መንገድ ባልተቃናበት ዘመን ከድምፅ የሚፈጥነው ሱፐር
ሶኒክ የጄት አውሮፕላን ባልታለመበት በዚያን ዘመን ከኢትዮጵያ ሊስቦን በሕንድ
በኩል ሄዶ መልእክት ለማድረስና ለማምጣት የአሥር ዓመት ጊዜ ሲፈጅ በአራት
መቶ ዓመት ውስጥ ዓለም በሥልጣኔ ተሻሽሎ ምን ያህል እንደተራመደ እንገነዘባ
ለን ።

በዚህም ላይ ከኢትዮጵያ በቀጥታ ፖርቱጋል በመርከብ ሄዶ መልእክት አድ
ርሶ ለመመለስ የሚፈጀው ጊዜ ከዚህ በጣም ያነሰ እንደሚሆን የታወቀ ነው ። ዳሩ
ግን የኢትዮጵያው መላክተኛ በፈረስ ወይም በበቅሎ ጀርባ ንጉሡ ካሉበት ከአንጾ
ኪያ (ይፋት) ወይም ከደብረ ብርሃን (ተጉለት) ተነሥቶ ምጥዋ ፣ ከምጥዋ ወደ ጎአ ፣

(1) Verdadeira ምዕ. 3

(2) " ምዕ. 9



የመለክተኞች መሪ ሮድሪጎ ዴ ሊማ ፡

ከዝኢ ወደ ሊስቦን ሲሄድና በዚህ መሥመር ሲመላለስ መርከብ ጥበቃው ከቱርኮ ችና ከዓረቦቹ ቍጥጥር ለማምለጥ ያለው ድብቆሽ ሲጨመር ከቀድሞው ደካማ የመገናኛ ድርጅትና አስተዳደር ጋር ብዙ ጊዜ መፍጀት አለበት ። የማቴዎስም ጕዞ በሊስቦንና በሮማ መካከል መልክተኞች የመላኩ ጉዳይ ሲመከር ሲዘከር ሌላ ጊዜ ሲፈጅም በሦስት ዓመት ውስጥ ሊፈጸም ይቻል የነበረው መልእክት ወደ አሥር ዓመት ሊራዘም የቻለው በዚህ ሁሉ ምክንያት ነው ።

አሁን ግን እነሆ እንደምንም የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ በመርከብ መልክተኞ ቹን ይዞ ምጥዋ ገብቶ ከሰነበተ በኋላ መልክተኞቹን በምን አኳኋን ወደ አፄ ልብነ ድንግል እንደላከ ከዚሁ ባለፈው ከጠቀስነው መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን እንደሚ ከተለው እንመልከት ።

«አገረ ገዢው ለባሕር ነጋሽ ንግሮት እንደነበረው . . . . . . ወደ ቍሱ (ዓፄ ልብነ ድንግል) መልእክቱን ለማድረስ ዶም ሮድሪግ ደ ሊማ (DOM RODRIGO DE LIMA) የሚባለውን መልካም ሰው ሾመ ።

እርሱንም የሚረዱ ዦርዥ ዳብሬ JORGE D' ABREU አንድ አስተር ጓሚ ከ፲፫ ሰዎች ጋር ሰጠው ። ከነዚህም ውስጥ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ (FRANCESCO ALVAREZ) አብሮ አለ ። ዶም ሮድሪግ ከአርኪቆ ለንጉሡ አገረ ገዥው የላከውን ገጸ በረከት ይዞ ተነሣ . . . . . . ገጸ በረከቱም ለንጉሡ የሚሰ ጠው አራት በረቂቅ የተሠሩ ሥጋጃዎች ፤ በቀይ ከፋይና በወርቅ ያጌጡ ጥሩሮች አንድ የወርቅ ሰይፍ ፤ አንድ የወርቅ ሳንጃ ፤ ሁለት መጻሕፍት ፤ ሁለት በርሜል ባሩድ ፤ አንድ በመስቀል የተመለከተ የፖርቱጋልን ንጉሥ የሕንድ ግዛት የሚያ ሳይ ያገር ካርታ ፤ የእመቤታችን ሥዕል ፤ የሙዚቃ መጫወቻዎች (ኦርጋና ክላቪርኮ ርን) አንድ በነዚሁ መጫወቻዎች ሊጫወት የሚችል ሙዚቀኛ ። ለንግሥት እሌኒ በአልማዝ ያጌጠ የሐር ሹራብ ፤ ከከበረ ድንጋይ የተሠራ መስቀል ፤ ለደብረ ቢዘን ገዳም ዕጣን ፤ ቁንዶ በርበሬ ፤ የሐር ግምጃ ፤ አንድ ደወል ፤ ለመነኩሳቱ የሚሆን አልባሳት ።

ከአርኪቆ ደብረ ቢዘን ከደረሱ በኋላ ዶም ሮድሪግ ተከታዮቹን እንደያዘ ወደ ንጉሡ ለመሄድ ጉዞውን ገሠገሠ ። በዚህ አውራጃ የሚገኙት የሞር ተወላጆች (ቱርክና ዓረቦች) እንግዲህ የፖርቱጋል ንጉሥና የኢትዮጵያው ንጉሥ ከተዛመዱ ያጠፉናል በማለት አዘኑ ። የፖርቱጋል ትልቁ መርከብ ምጥዋ ድረስ መጥቶ ይኸን ያህል ከሠራ ወደፊት ወደ ሱዌዝም ሄዶ የሃይማኖታችን ፍጻሜ ይሆንን በማለት ምልክቱ የደረሰ መሰላቸው ። በዚህ ምክንያት ፍርሃት ስለአደረባቸው የዳሕላቅን ደሴት ትተው እየሸሹ ወዳገር ውስጥ ገቡ ። የፖርቱጋሉ አገረ ገዥ የደሴቱን መለ ዮቶ ሲያይ በደሴቱ ሁሉ ላይ ያለውን አቃጠለው ። . . . . ከዚያ በኋላ ወደ ኦርሙዝ ሄደ» (፩) ።

እንግዲህ እ.አው.ቀ. የካቲት ፲፫ ቀን ፲፭፻፳ ዓ.ም. አገረገዥው ዲዬጎ ሎፔዝ

(፩) አልቫሬጽ ምዕ. 5 - 6 Castanheda በፈረንሣዊው ትርጉም ምዕ. 10

፳፬ የጦር መርከብ (VAISSEAUX) ይዞ ከጎአ ተነሥቶ በዚሁ ዓመት ሚያዝያ ፲ ቀን ምጥዋ ገብቶ የቱርክን የጦር ኃይል አሸንፎ ምጥዋን ከያዘና ካረጋገጠ በኋላ ወደ ዓፄ ልብነ ድንግል የሚሄዱትን መልክተኞች አስናብቶ የንጉሡን ትእዛዝ እፍ ጸሚ አድርሶ ወደ አርሙዝ ደሴት ከዚያም ወደ ጎአ ተመልሷል ። አርሙዝ ወይም ሖርሙዝ በሕንድ መንገድ ላይ በፋርስ ግዛት አጠገብ የምትገኝ ደሴት ናት ።

፳፬ የጦር መርከብ ይዞ ራሱ አገረ ገዥው ወደ ምጥዋ መምጣቱ የፖርቱጋል ንጉሥና መንግሥቱ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሊያደርጉ ያሰቡትን ግንኙነት ምን ያህል በቁም ነገር እንዳሰቡበት ያሳያል ። በምጥዋ ለጊዜው የነበሩትም የቱርክ ሁለት ታላላቅና ብዙ ትናንሽ መርከቦች እነዚህን ለመቋቋም ኃይል ስላልነበራቸው ጸሐፊው እንዳለው ገና በሩቅ ሲያዩ መሸሻቸው የሚመስል ነው ። እንደዚሁም የፖርቱጋል ኃይል ምጥዋ ሲገባ የክርስቲያኑ ወገን ሲደሰት ፤ የእስላሙ ወገን የቻለው አሜን ብሎ መቀበሉና ማስተናገዱ ፤ ያልቻለውም መሸሹ የቀረውም እን ግዲህ መጥፊያችን ደርሶ ይሆን እያለ ለጊዜው መጨነቁ የማይቀር ነው ።

ዳሩ ግን የወደፊቱ ጊዜ ለእስላሞቹ አደገኛ የመጥፊያ ጊዜ በመሆን ፋንታ ለክ ርስቲያኖቹ ላፄ ልብነ ድንግልና ለመኳንንቶቻቸው ለሕዝቡም ጭምር የጦርነት የሁከት የመከራና የስደት ዘመን መሆኑን ወደፊት በሚከታተሉት የግራኝን ጦር ነት በሚተርኩት ምዕራፎች ላይ እንመለከታለን ።

እስከዚያ ወደ መልእክተ[illegible]ጉዳይ ተመልሰን ወደ አፄ ልብነ ድንግል ለመ ሄድ ያደረጉትን ጉዞ እንመልከት ።

የሕንድ አገረ ገዥ ዲዬጎ ሎፔዝ ምጥዋ አድርሷቸው ከባሕር ነጋሽ ጋር በውል ተነጋግሮ ወደ ግዛቱ ከተመለሰ በኋላ መልክተኞቹና ዋናው እምባሳደር ሮድሪጎ ከምጥዋ ወደ ባሕር ነጋሽ ከተማ ወደ ደባሩዋ ሄደው በነበረበት ጊዜ የራሳ ቸውን ጓዝና ስንቅ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚሰጠውን ገጸ በረከት የሚጭኑበት ከብት ለማግኘት ብዙ ጊዜ በደጅ ጥናት እንደተቸገሩ ባለፈው ምዕራፍ ላይ በኑሮ ደረጃ ምክንያት ጠቅሰነዋል ።

ወደ ባሕር ነጋሽ ቤት በሄዱ ጊዜ አንድ አንድ ጊዜ ከልካይ አላስገባ እያላቸው አንድ አንድ ጊዜ ደግሞ ባሕር ነጋሹ ዓይኔን አሞኛልና አታስቸግሩኝ እያለ ጉዳያቸ ውን ሳይፈጽም እንደመለሳቸው ደግሞ በመካከሉ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ትልቅ ሰው እየመጣ እርሱን በማስተናገድ የነርሱ ጉዳይ ችላ እንደተባለና በዚሁ እንግዶቹ ከማረፊያ ቤታቸው ዕቃው ወደተቀመጠበት ፤ ከዚያ ደግሞ ለደጅጥናት ወደ ባሕር ነጋሽ ቤት መመላለሱና ደጅ ጥናቱ ትዕግሥታቸውን ስለጨረሰው «ይህ ዕቃ ከፖ ርቱጋል ንጉሥ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የተላከ በመሆኑ ተሸካሚ ይታዘዝልን ያለዚያ ግን ይኸን ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆንህን ቁርጡን ንገረንና ዕቃውን አቃጥለን ወደ መጣንበት አገር እንመለሳለን» ብለው ከብስጭት የተነሣ እስከ መናገር መድረሳቸውን አልቫሬዝ በመጽሐፉ በዝርዝር ያመለክታል (1) ።

(1) ምዕራፍ 27 - 28

ባሕር ነጋሽ ዶሪ በኢትዮጵያ መንግሥትና በፖርቱጋል መንግሥት መካከል የተወጠነው ይህ ወዳጅነት ምን ያህል ቀም ነገር ያለው መሆኑን እንደማይስተው የታወቀ ነው ። ራሱ የሕንድ አገረ ገዥ ከጎአ ድረስ በመርከብ መጥቶ እነዚህን ሰዎች ባስረከበውና ውልም በተዋዋሉ ጊዜ ዝርዝሩን ሁኔታ የጉዳዩን ክባድነት በመረዳትና እነዚህን ሰዎች አከባክቦ በማስተናገድና በደስታ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ በመላከ ፈንታ እንደዚህ አድርጎ ደጅ ያስጠናበት ምክንያት አይገባንም ። በዚሁ መጽሐፉ ላይ አልቫሬጽ ባሕር ነጋሹ ልጁን ስለገደሉበት ወደ ኑብያ ለመዝመት ይዘጋጅ ነበር ብሎ ጠቅሷል ። ይኸም ባገርና በመንግሥታዊ ደረጃ ሲመዘን በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም ። በመጨረሻም ዕቃ የሚጭኑበትን አጋሠሥ ስጠን ቢሉት እናንተው ማዛት አለባችሁ ብሏቸው በመጨረሻ ራሳቸው አጋሠሦች ገዝተው ከባሕር ነጋሹ ፲ ግመሎች ብቻ ተዳርገው በነዚህ ዕቃቸውን ጭነው በመጨረሻ በሰኔ ወር በክረምቱ ከደባርዋ ተነሥተው ተጉዘው ማይ ፀዓዳ (ጥሩ ውኃ) ከሚባለው ከተማ መድረሳቸውንና የዚህ ወረዳ ገዥ በመልካም ተቀብሎ እንዳስተናገዳቸው አልቫሬጽ ይገልጣል (1) ።

ከዚያ በየመንገዱ በየከተማው እየዋሉና እያደሩ አክሱም ከተማ ደርሰው ታሪካዊቷን ከተማ ከጐበኙ በኋላ በአምባ አላጌና በአሸንጌ በላስታ በኩል አድርገው ደብረ ሊባኖስ (ሰላሌ) ደረሱ ። በዚህም ወር በደብረ ሊባኖስ እጨጌ ጴጥሮስ ሞተው በርሳቸው ፈንታ የሚተኩትን ለመምረጥ ስብሰባ ተደርጎ እጨጌ ዕንባቆም ተመርጠው ደስታ ሆኖ ነበርና ለዚሁ የተሰበሰቡት ሊቃውንትና መነኰሳት እንግዶቹን በመልካም ተቀብለው አስተናገዷቸው (2) ።

በአቡነ ጴጥሮስ ፈንታ አዲስ ለእጨጌነት የተመረጡት አባ ዕንባቆም ዘራቸው ዓረብ ነው (3) ። በንግድ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ክርስትናን ተቀብለው በኢትዮጵያ ትምህርት ሊቅ ሆኑ ። ከዚያም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው ምንኵስናን ተቀብለው ሲኖሩ እነሆ አሁን ለእጨጌነት ተመርጠው በመንበረ ተክለ ሃይማኖት ለመቀመጥ በቁ ።

እርሳቸውም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የታወቁ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጐሙ ናቸው ። ከነዚህም የታወቁት ቀድሞ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን የጻፈውን መልእክት በኋላ ዮሐንስ አፈወርቅ ሐተታ እየሰጠ ያዘጋጀውን አባ ሚካኤል ግብፃዊ ከሚባል ጋር ተርጉመዋል ። ለዚሁም ማስረጃው በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ «ተተርጐመት እምልሳነ ዓረቢ ለግዕዝ በእደ ዕንባ

(1) ምዕራፍ 30

(2) ዝ. 67

(3) እርጌውና የሞቱት እጨጌ ጴጥሮስ መሆናቸውን ብላቴን ጌታ ኅሩይ በዋዜማ መጽሐፋቸው በገጽ 110 ላይ ስለገለጹ አልቫሬጽ በዚሁ በ67 ምዕ. ላይ እርጊው እጨጌ ዮሐንስ ይባላሉ ያለው ስሕተት መሆን አለበት ።

ቆም ወሚካኤል ግብፃዊ» ይላል (1) ። እንደዚሁም ባፄ ገላውዴዎስ ትእዛዝ የበ ረላዓምንና የዮሳፍጥን መጽሐፍ (በርላም ወይዋስፍ) ተርጉመዋል ። ምስተር ውልያም ራይት ፲፰፻፸፯ ባወጡት የኢትዮጵያ መጻሕፍት ዝርዝር በገጽ ፪፻፬ ላይ ስለዚሁ መጽሐፍ አተረጓጐም እንደዚህ ይላል "ተፈጸመ ገድሎሙ ለቅዱሳን በረ ላይ ወይዋስፍ (በረላዓምና ዩሳፍጥ) በሰላም . . . ." ይልና ዝቅ ብሎ "ተተረጐመ ዝንቱ መጽሐፍ እምልሳነ ዓረቢ ለግዕዝ በትእዛዘ ንጉሥነ መፍቀሬ እግዚአብሔር ገላውዴዎስ . . . . ወተርጐሞ ዕንባቆም ምስኪን ለግዕዝ እምዓረቢ ።" እንደዚሁም ራሳቸው አንቀጸ አሚን (የሃይማኖት በር) የሚባለውን ደርሰዋል (2) ። ስለዚህ እኚህ እጨጌ ዕንባቆም በዚህ ዘመን የኢትዮጵያን ግዕዛዊ ሥነ ጽሑፍ ካስፋፉት ዋነኛው ናቸው ማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፲፱

### የፖርቱጊዞቹ ሸዋ መድረስ — ባፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት የገጠማቸው ቀዝቃዛ መስተንግዶና የረዥም ቀን ደጅ ጥናት (፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ጥቅምት ፱ ቀን )

መልክተኞቹ ከደብረ ሊባኖስ ንጉሡ ወደአሉበት ወደ እንጾኪያ (ደፋት) ደረሱ ። የደረሱበት ጊዜ እ.አው.ቀ. ጥቅምት ፲፪.ቀን.፲፭፻፳ ዓ. ም. መሆኑ በነርሱም መጽ ሐፍ ስለተገለጸ እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ጥቅምት ፲ ቀን ፲፭፻፲፫ ዓ. ም. መሆኑ ነው ። ዳሩ ግን ፖርቱጊዞቹ የጦር መሣሪያ በብዙ ይዘው ይመጣሉ ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ሳያመጡ በመቅረታቸው ይሁን ፤ ወይም ምጥዋ ከፖርቱጋሉ አገረ ገዥ ለን ጉሡ ለማቅረብ ከተቀበሉት ገጸ በረከት ግማሹ በየመንገዱ ባክኖ በዚሁ በንጉሡ ዘንድ ቅርታ ገብቶ ይሁን ሳይታወቅ ለነዚሁ ከሩቅ አገር ድልቁንም ለዘምድና ከተ ፈለገው ከፖርቱጋል መንግሥት ዘንድ ለመጡት መልክተኞች መልካምና ደንበኛ አቀባበል አላደረጉላቸውም ።

ከመልክተኞቹ አንዱ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በኢትዮጵያ ፮ ዓመት ከቆየ በኋላ ሲመለስ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. (ስለቄሱ ዮሐንስ አገር እውነተኛው ወሬ) በሚል አርእ ስት ባወጣው መጽሐፍና ሕንድን የማግኘትና ድል የማድረግ ታሪክ በሚባለው በደካስታንሄዳ መጽሐፍ ላይ ስለአቀባበሉ ጉዳይ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል ።

«ንጉሡ እኛን ለመቀበል ታላቅ በዓል እንዲሆን አድርጓል ። የንጉሡ ቀይ ቀለም ያለው ታላቅ አዳራሽ ያለው ድንኳን በመካከል ሆኖ ዙሪያውን ሌሎች ነጭና ቀይ ቀለም ያላቸው ድንኳኖች ተተክለዋል ። ንጉሡ በታላቁ ድንኳን ውስጥ ዙሪያ ውን በመጋረጃ ተከልሎ በውስጠኛው ተቀምጧል ። በውጭ ያለው ሕዝብ ቁጥሩ

(1) Catalogue des manuscripts—Zotenberg ገጽ 74 ። Catalogue of the ethiopic manuscripts......W.Wright ገጽ 204 - 205

(2) Storia della Letteratura etiopica-ignazio Guidi: ገጽ 72 - 73

እጅግ ብዙ ነው ። ሕዝቡም ወደፊት እንዳይገፋ ከልካዮች ይጠብቁታል ። በመገ
መሪያው ረድፍ (ደረጃ) የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሹማምንት የበዓል ልብ
ሳቸውን ለብሰው ይታያሉ . . . በንጉሡ ድንኳን በራፍ አጠገብ የንጉሡ አራት የሚ
ያማምሩ ፈረሶች ግሩም የሆነ ዕቃና ኮርቻ ተጭነው ቆመው ይታያሉ ። ከነርሱ
በታች አሥር ሺ የሹማምንት ፈረሶች ተሰልፈው ይታያሉ ። በንጉሡ ፈረሶች
ፊትና ኋላ የቤተ መንግሥቱ ሹማምንት ነጫጭ ልብሳቸውን አደግድገው ቆመ
ዋል ። ሌሎች ደግሞ ጐፈር የለበሱ በእጃቸው አለንጋ ይዘው ንጉሡ በሚያልፍበት
ጊዜ ሕዝቡን የመከልከል (የማጋፈር) ተግባር ያላቸው ይታያሉ ። . . . ከዚያ መቶ
የሚሆኑ ከልካዮች በሕዝቡ መካከል እየቀደዱ አልፈው ዙፋኑ ወዳለበት ፊት ለፊት
. . . . . . ሲደርሱ ሁሉም እጁ መሬት እስኪነካ ድረስ በጥልቅ እጅ ሲነሣ መላክተ
ኞቹም እንደዚሁ ባክብሮት እጅ ነሡ ። በንጉሡና በነርሱ መካከል የሚያምር መጋ
ረጃ ስላለ ንጉሡ አይታይም ። በመልክተኞቹ ግራና ቀኝ የልዩ ልዩ አውሬ ቆዳ በር
ኖስ ካባ በላዩ ላይ ጥልፍና ክፈፍ የብርና የወርቅ ቁልፍ ያለው የለበሱ ሠራተኞች
ሁሉም በያለበት እየተዘዋወሩ ሥራቸውን ያስተናብራሉ ። እነርሱም በግራና በቀኝ
ሆነው መላክተኞቹን ወደ መጀመሪያው አጥር አገቡዋቸውና በዚያ አቆዩዋቸው ።
የመግቢያው በር በሰንሰለት በታሠሩ አራት አንበሶች ይጠበቃል ። በመላክተኞቹ
ፊት ለፊት ወደ ንጉሡ ለመቅረብ የሚችሉ ዙፋኑንም የሚጠብቁ አራት ባለሥል
ጣናች ይገኛሉ ። መላክተኞቹ አስገቢዎቹ የልፍኝ አሽከሮች የሚያደርጉትን እየተ
ከተሉ ለጥ እያሉ ለማይታየው ለግርማዊነቱ እጅ ነሡ ።

በዚያን ጊዜ ትንሽ ፀጥታ ከሆነ በኋላ በዕድሜ የሸመገለ መነኰሴ የቤተ መን
ግሥቱ ዓቃቤ ሰዓት የሚባለው ፪ኛው ባለሥልጣን ከድንኳኑ (ንጉሡ ካሉበት
ማለት ነው) ብቅ አለና "እነማናችሁ ከወዴትስ መጥታችኋል" ብሎ ጠየቀ ። ይኸ
ንንም የጠየቀው ሥርዓት ለመፈጸም እንጂ ከወዴት እንደመጡ እነማን መሆናቸ
ውም ታውቋል ይሁን እንጂ ዓቃቤ ሰዓቱ መልሱን ካገኘና ወደ መጋረጃው ገብቶ
ለጌታው ከነገረ በኋላ እንደገና መጥቶ ይኸንኑ ጥያቄ ፫ ጊዜ አቀረበ ። በ፫ኛው
ጥያቄ ላይ ዋና መልክተኛ ገርሞት እየተቆጣ እንደዚህ አለ "እንግዲህ ምን ልና
ገር እችላለሁ" አለና ዝም አለ ። ዓቃቤ ሰዓቱ የመጣችሁበትን ጉዳይ ለግርማዊነታ
ቸው እንድነግርላችሁ አስታውቁኝ አለ ።

ከዚህ በኋላ ዋናው መላክተኛ ዶም ሮድሪግ (Dom Rodrigue) የተላከሁ
በትን ጉዳይ ከንጉሡ በቀር ለሌላ አልነግርም ። ከዚህም ጋር ከግርማዊነታቸው ተገና
ኝቼ ንጉሣዊ እጃቸውን ስሜ ስለክርስቲያኖች የቃል ኪዳን አንድነት ፣ ስለሕዝቡም
ብልጽግናና ስላገሩ ልማት ምኞቴን ማቅረብ እፈልጋለሁ ብሎ መልስ ሰጠ ። ዓቃቤ
ሰዓቱ ይኸን መልስ ለንጉሡ ከነገረ በኋላ ተመልሶ ከሕንድ ከንጉሡ እንደራሴ የመ
ጣውን ገጸ በረከት እንድታቀርቡ ንጉሡ አዘዋል አለ ። በዚህ ጊዜ ሮድሪግ ለንጉሡ
እንጂ ላንተ አላስረክብም ብሎ ነበር ። በኋላ ግን ወገኖቹ ስለመከሩት እሺ አለና
ገጸ በረከቱ እየተቆጠረ እንደጠረጴዛ አለው እንጨት ላይ ተደረደረ ። ለገጸ በረከት
የተደረደረውን የሐር ልዩ ልዩ ልብስ በማየት ከውጭ የሚመለከተው ሕዝብ አድ

ናቆቱን በድምፁ ሲገልጽ ይሰማ ነበር ።

ከዚህ በኋላ ዓቃቤ ሰዓቱ ተመልሶ እግዚአብሔር ይስጣችሁ አለና ያቀባበሉ በዓል በዚሁ ብቻ አለቀና ንጉሡንም ሳይገናኙ ሌላም ንግግርና ጭውውት ሳይጨመርበት መላክተኞቹ ወደ ሠፈራቸው እንዲመለሱ አጋፋሪዎቹ አመለከቷቸው ። ወደ ሠፈር ሄደው ትንሽ እንደቆዩ ድርጎው ተቀጣጥሎ እሠፈር ድረስ መጣ (1)» ።

እስካሁን ያለውን ሁሉ ስንመለከት እቴጌ እሌኒ ከአሥር ዓመት በፊት ማቴዎስን ወደ ፖርቱጋል ሲልኩ አፄ ልብነ ድንግል ገና ወጣትና የመንግሥቱን ሥልጣን እንዳልጨበጡና የእቴጌ እሌኒንና የማቴዎስን ድካም በዚህ ግንኙነት ምክንያት የሚገኘውንም ከፍ ያለ ጥቅም እንኳን በወጣትነታቸው ጊዜ አሁንም በዕድሜ ፳፫ ዓመት ደርሰው ሥልጣን በያዙበት ጊዜ ሁሉ እንዳላመዛዘኑትና ዋጋ እንዳልሠጡት ያስረዳል ። ምንም እንኳን በመዠመሪያው ዶኮቪልሐእን ልኮ ግንኙነቱን የወጠነው የፖርቱጋል መንግሥት ቢሆንም «ልጆቻችንን ከልጆቻችሁ እናጋባና ኃይላችንንና ኃይላችሁን አንድነት አድርገን የሁላችንንም ጠላት እስላምን እናጥቃ» የሚል የጥያቄ ቃል ለፖርቱጋል ንጉሥ የተጻፈው ከኢትዮጵያ መንግሥት ወገን ነው ። የፖርቱጋል ንጉሥ የኢትዮጵያን መላክተኛ ማቴዎስን በክብር ተቀብሎ ራሱ አነጋግሮ እንዳንድ መስፍን ሲያንከባክብ ሰንብቶ በመጨረሻ የራሱን መላክተኛ ሲልክ መላክተኛ፺፯ በፍቅር ዕለቱን ተቀብሎ አነጋግሮ በማስተናገድ ፈንታ ይኸን የመሰለ ያልታሰበ ሁኔታ ሲደርስባቸው ከንጉሡ ተገናኝተው እጅ መንሳትና መነጋገር ሲከለከሉ፤ እንዳልታወቀ ሰው ከወዴት መጥታችኋል እየተባሉ ሲጠየቁ በዚያን ጊዜ የሚሰማቸውን ቅርታ ለመገመት አያስቸግርም ። በገጸ በረከቱም በኩል ቅርታ ቢኖር ቅርታውን ያላለፉት ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያ የተለመደው ሁል ጊዜ ከባድ ቢሆንም ለነዚህ ከሩቅና ከወዳጅ አገር ለመጡት ያላቀለሉበት ምክንያት ሊገባን አይችልም ። ከዚህ በፊት የጠቀስነው ያ ቸልታውና ከንቱ ውዝግብ የሞላበት የመንግሥቱ አቀዋም እዚህ ላይ ይታያል ።

ከዚህ አያይዞ ደ ካስታንሄዳ በመጽሐፉ እንደዚህ እያለ በመቀጠል የመጨረሻውን አቀባበል ይተርካል ።

«. . . ገጸ በረከቱን ዶም ሮድሪግ እንደተጠየቀው ለዓቃቤ ሰዓቱ ካቀረበና እርሱም ወስዶ ለንጉሡ ካሳዩ በኋላ በቅስቱ ሥር አስቀመጠና ዝም በሉ ብሎ አዘዘ . . ከዚያ ትልቁ ዳኛ (ጸሐፊ ላም ይሆናል) ዕቃውን በየስሙ እየጠራ ቆጥሮ ሲጨርስ በታላቅ ድምፅ እንደዚህ አለ "በክርስቲያኖች መካከል ስለተደረገው ዝምድና ሁሉም ለጌታ ምስጋና ሊያቀርብ ይገባዋል ። በዚህ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ይህ ነገር ያሳዘነው ቢኖር ያልቅስ ያስደሰተው ደግሞ ይዝፈን" እርሱም ንግግሩን ሲያቆም ሕዝቡ አምላኩን በማመስገን ደስታውን በጩኸት ገለጠ . . . . ዶም ሮድሪግ ፲፩ ቀን ሳይገናኝ በቤተ መንግሥቱ ደጃፍ እንደሰነበተ ረቡዕ ዕለት

(1) Histoire de la decouverte et de la conquête de l'inde (extrait) Verdadeira.... ምዕ. 70 - 75 ገጽ 138 - 140 ።

ኅዳር ፲ ቀን ከሌሊቱ በ፪ ሰዓት (፰ ሰዓት) ተጠራ . . . እርሱም እንግዲህ ልገናኝ ይሆናል ብሎ በቶሎ አጥር ውስጥ ወዳለው ወደ ንጉሡ ድንኳን አመራ . . . ነገር ግን ሲደርስ በረኞቹ አናስገባም ብለው በሌሊት እከፋ ብርድ ላይ አንድ ሰዓት አቆሙት ። ከርሱ ጋር ያሉት ቢቸግራቸው (መኖራቸውን ለማስታወስ ያህል) ጥይት ወደ ሰማይ ተኰሱ ። ከዚያ ከንጉሡ ዘንድ አንድ ሰው ተልኮ መጥቶ ለምን ብዙ ጠበንጃ አላመጣችሁም ብሎ ጠየቀ ። ዶም ሮድሪግም ለመልከተኞቹ ለጦርነት አልመጣንም ሲል መለሰ ። ከዚህ በኋላ ማዝርዶም (የልፍኝ አስከልካይ) እና አራት የቤተ መንግሥቱ ሹማምንቶች መጥተው ሮድሪግንና ሰዎቹን ጠርተው ከፊት ማዝርዶሙ ከኋላ አራቱ ሹማምንት አጅበው ሁለት ሰዎች ደግሞ የጢፍ መብራት ይዘው ወደውስጥ አስገቧቸው ። የመዠመሪያውን ቅጥር አልፈው ወደ ሁለተኛው ቅጥር ሲገቡ ሹማምንቶቹ ቆም እያሉ በየተራ "ጌታ ሆይ አምጣቸው ያሉኝን አመጣሁልዎ" ሲል ከውስጥ "ግቡ" የሚል ድምፅ ይሰማል ። ይኸም ንጉሣዊ ድምፅ ስለሆነ ሹማምንቱ በቀኝ እጃቸው መሬት እየነኩ እጅ ይነሣሉ ። ይኸም የጥያቄና የመልስ ሥነ ሥርዓት ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ በመጨረሻ ማዝርዶሙ (ጽራግ ማሠሬው ?) ጌታ ሆይ አምጣቸው ያሉኝን ፈረንጆች አመጣኋቸው ሲል ከውስጥ ግቡ የሚል ቃል ተደጋግሞ ከተሰማበኋላ ወደቤት ገቡ . . . ። በቤቱ ውስጥ አንድ በመልካም የተዘጋጀ ከፍተኛ ቦታ (ዙፋን) ይታያል ። በርሱ ፊት ለፊት በቀኝ ፺ በግራ ፺ በድምሩ ፻፹ ሰዎች መብራታቸውን ይዘው ቆመዋል ። ወለሉ በባለ ቀለም ሰሌን ተሸፍኗል ። ሁሉም እዚህ ክፍል ሲደርስ ቆመ ። አንድ የልፍኝ አሽከር ከንጉሡ ዘንድ እንደዚህ የሚል መልእክት ለሮድሪግ ይዞ መጣ . . . የፖርቱጋል ንጉሥ የላከልኝን ገጸ በረከት ለምን አትሰጡኝም . . . ሮድሪግም እንደ ዚህ ብሎ መለሰ ያገረ ገዥው መርከብ ምጥዋ የገባው ለመዠመሪያ ጊዜ በመሆኑ ምጥዋ ለማራገፍ እርግጠኛ አልነበረም ። ስለዚህ እነዚያን (በፊት ያስረከባቸውን) ብቻ ላከ ። ነገር ግን በርግጥ ወደፊት ይደርሳሉ ። በዚህ ምክንያት ንጉሡ ሳይታይ አሰናብቶ መለሳቸው . . . ከ፪ ቀን በኋላ እንደገና በሌሊት ሮድሪግ ተጠርቶ ፖርቱጊዞች የሰይፍ አመታትና አመካከት እንዲያሳዩ ተጠየቀና ሁለት ሞፍሮቹን እንዲያሳዩ አደረገ ። ነገር ግን ያንደኛው ሥራ ልቡን ስላላስደሰተው ራሱ ገብቶ ከጸሐፊው ከዦርዥ - ዳብረ ጋር አሳይቶ ሲጨርስ ይኸን ለንጉሡ ብዩ ነው እንጂ እማንም መስፍን ፊት አላደርገውም ነበር . . . አሁንም ኧረ እባክዎ ተቀብለው አነጋግረው በጊዜው መርከብ አግኝቼ እንድመለስ ያሰናብቱኝ ብሎ ቢልክ ንጉሡ ሳይቀበሉ መለሱት . . . . . ከዚያ እንደገና ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ (ለብቻው) በንጉሡ ተጠርቶ ያገሩ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት የአለባበሱስ ነገር እንዴት እንደሆነ በመልእክት ተጠይቶ ካስረዳ በኋላ ፖርቱጊዞቹን ደህና አስተያየት አደረጉላቸው . . .» (1)

ISIC

አልቫሬጽ በበኩሉ በመጽሐፉ ከዚህ በላይ ያለውን ከተረከ በኋላ እንደገና ከዶም ሮድሪግ ጋር ተጠርተው ሄደው በቤተ መንግሥቱ በራፍ ላይ በቆሙበት

(1) Verdadeira ምዕራፍ 74 - 75 ። ካስታንሄዳ ገጽ 140 - 141

ሰዓት አብዲናን የሚባለው የብላቴናች ሹም (የልፍኝ አሽከሮች አለቃ) በንጉሡ ስም መጥቶ ብዙ ጥያቄ አቅርቦ የመልክተኞቹ አለቃ ሮድሪግ እንደመለሰለት ይገልጽና ጥያቄና መልሱ ከዚህ እንደሚከተለው መሆኑን ያመለክታል ።

«ጥያቄ - ስንት ናችሁ ፤ ስንት ጠመንጃ ይዛችኋል ፣ ለእስላሞች ጠመንጃ መሥራት ያስተማራቸው ማነው ፖርቱጋሎቹና እስላሞቹ ቢዋጉ ማን ያሸንፋል ?

መልስ - እኛ ፖርቱጊዞች በኢየሱስ ክርስቶስ የጸናን ስለሆንን እስላምን አንፈራም . . . የምንፈራ ብንሆን ኖሮ ያን ሁሉ አገር አቋርጠን ወደ እናንተ ለመምጣት ባልደፈርን ስለእስላሞች መሣሪያ መሥራት መቻል ለተጠየቅነው እነሱም እንደኛው ሰዎች ስለሆኑ ዕውቀትም መሣሪያም አላቸው ።

ጥያቄ - ቱርኮችስ ጥሩ ነፍጥ አላቸውን ?

መልስ - የቱርኮች ነፍጥ ጥሩና ከኛም የሚመሳሰል ነው» (1) ።

ንጉሡ ንግሥቱና ባለሥልጣኖቻቸው ይኸን የመሰለውን ጥያቄ ከማቅረብ በፊት እንግዶቹን በቅድሚያ ተቀብሎ ማስተናገዱ በተገባ ነበር ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር ግንኙነቷ ተቋርጦ የኑሮ ደረጃዋ በማናቸውም መሥመር ዝቅ ያለ ስለሆነ የውጭን አገር እንግዳ በሌሎቹ በሠለጠኑት አገሮች እንደሚደረገው ተቀብሎ ማስተናገዱን ሳይረዱት ቀርተዋል ማለት ነው ። ያለዚያ ይህ ከአቀባበል በፊት የቀረበው ጥያቄ ከገበታ ላይ በመብልና በጨዋታ ጊዜ ሊቀርብ በቻለ ነበር ።

ISIC

እንግዶቹን ከመቀበል በፊት ንጉሡ ንግሥቱ በመልክተኛ በኩል ይኸን ጥያቄ ሲያቀርቡ አሳባቸው ፖርቱጋሎቹ "በመሣሪያ ሥራና በዠግንነት" ከኛ ቱርኮች ይበልጣሉ ያሉ እንደሆነ እንግዲያውስ አንፈልጋችሁምና በመጣችሁበት መንገድ ተመለሱ ለማለት ይሆን ? ወይም እኛ እንበልጣለን ቢሉ ከነርሱ ጋር በተወጠነው ዝምድና ለመተማመንና እንግዶቹን በመልካም ተቀብሎ ለማስተናገድ ይሁን አይታወቅም ።

ዳሩ ግን ማንም ቢሆን በዕውቀትና በጉልበት ካንተና ከጠላትህ ማናችሁ ትበልጣላችሁ የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡለት በተለይ በዚህ በመንግሥት ደረጃ ለመጣ መልክተኛ ጠላቴ ነው የሚበልጠው የሚል ስለሌለ ለፖርቱጊዞቹ የቀረበው ጥያቄ ዋጋ ቢስ ነው ። መልክተኛው የመለሰውም እንዳለው ከሆነ ትክክለኛ መልስ ሰጧል ለማለት ይቻላል ።

(2) Verdadeira ..... ባቶ ገርማ በሻህ ትርጉም ምዕ. 76

## ምዕራፍ ፳

## በመጨረሻ አፄ ልብነ ድንግል መልክተኞቹን እንደተቀበሏቸው

## (፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ኅዳር ፲፱ ቀን)

ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው ተቀብለው ባያነጋግሩዋቸውም ወደ ቤተ መንግሥቱ እየተጠሩ በዓቃቤ ሰዓቱና በእልፍኝ አስከልካዩ በኩል ብዙ ጊዜ የአሳብና የንግግር መለዋወጥ ጉዳይ ሲቀጥል ሰንብቶ በዚህ መካከልም ከዋናው መላክተኛ ከዶም ሮድሪግ ይልቅ የቤተ ክህነቱ ሰው አልቫሬጽ ሞገስ አግኝቶ ከንጉሡ ጋር ስለመንፈሳዊ ጉዳይ በመነጋገር ዕድል አግኝቷል ። ይኸም የሚያመለክተን አፄ ልብነ ድንግል በዚህ ጊዜ ከፖለቲካና ከወታደርነቱ ጉዳይ ይልቅ ባለፉት ምዕራፎች እንዳመለከትነው ለመንፈሳዊና ለቤተ ክህነቱ ጉዳይ አሳቢ መሆናቸውን ነው ።

ይሁን እንጂ ዋናው መልክተኛ ዶም ሮድሪግ ከአልቫሬጽ ጋር ደብዳቤውን እንዲያቀርብ ተጠርቶ ከቀረበ በኋላ ደብዳቤውን ንጉሡ ከመቀበላቸው በፊት የተጻፈው በፖርቱጋል ቋንቋ ስለሆነ ንጉሡ ጉዳዩን በትክክል እንዲረዱት ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ ይተርጐም ተብሎ መመለሳቸውን ፤ በሚመለሱበትም ጊዜ ዋናው መላክተኛ «የኛ ቄሶች እንደአገራችን ልማድ ቅዳሴ እየቀደሱ ጸሎት እንዲያደርጉ ይፈቀድልን» የሚል ልመና አቅርቦ «እንኳን እናንተ ክርስቲያኖቹ እስላሞቹ እንኳን አይከለከሉም አሁንም እንደልማዳችሁ ጸልዩ» ተብ[illegible]ንደተፈቀደላቸው አልቫሬጽ በመጽሐፉ ያረጋግጣል (1) ።

ከዚህ በኋላ እ. አው.ቀ. ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፭፻፳ ዓ.ም. ማክሰኞ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ መላክተኞቹንና ከሕንድ የንጉሥ እንደራሴ ዘንድ በፖርቱጋል ንጉሥ ስም የመጣውን ደብዳቤ በይፋ ለመቀበል ስለወሰኑ መላክተኞቹ ሁሉም ባንድነት ተጠሩ ። ስለዚህ አቀባበል በኛ በኩል በታሪክ ነገሥት ውስጥ ሁለት መስመር እንኳን የታሪክ ጽሑፍ ስለሌለን የዚህኑ የአልቫሬጽን አጻጻፍ መቀበል ግዴታ ነው ። እርሱም እንደዚህ ይላል «ማክሰኞ ዕለት አምባሳደሩና አብረን የነበርነው መልክተኞች ተጠርተን ቀረብን . . . ከዚያ በፊት እየተጠራን ስንገባ ካየናቸው የበለጡ መጫሪያ የያዙ ብዙ ሰዎች ቆመው አየን . . . . በበሩም ፊት ለፊት ብዙ የጧፍ መብራቶች በርተው ይታዩ ነበር . . . ከበሩ ላይ ብዙ ሳያቆሙን ከአምባሳደሩ ጋር ዘጠኝ ፖርቱጊዞች የሆንነውን ከመዠመሪያው መጋረጃ ውስጥ አስገቡን ። ከነዚህ ከመዠመሪያዎቹ መጋረጃዎች አልፎ የሚገኙ ሌሎች ጌጠኞቹ መጋረጃዎች ነበሩና እነሱን አልፈን ሰፋፊ ሥጋጃ ወደተነጠፈበት አዳራሽ ገብተን ቆምን ። በቆምንበት ጊዜ መጋረጃዎች ግራና ቀኝ እየተሰበሰቡ ሲገለጡ ንጉሠ ነገሥቱን በጣም ካጌጡ ስድስት እርከን (ደረጃዎች) ካሉት መደብ (ዙፋን) ላይ ተቀምጠ አየነው ። እርሱም ከወገቡ በላይ በወርቅ ከወገቡ በታች በብር አምሮ የተሠራ ዘውድ አድርጓል ። በእጁም የብር መስቀል ይዟል ። አፉና አገጩ በሰማያዊ ሻሽ ቢሸፈንም አንዳንድ ጊዜ ሲገ

(1) Verdadeira ምዕ. 76

ለጥ ፊቱ በሙሉ ይታይ ነበር . . . . ሰፋፊ የሆነ የሐር ሸሚዞች ለብሶ በዚያ ላይ ካባ
ደርቧል ፡፡ ከታችም እግሩ በሙሉ ስለተሸፈነ አይታይም ፡፡ መስቀል ይዞ ከቆመው
የእልፍኝ አሽከር በቀር ጕራዴ ይዘው ከዙፋኑ ግራና ቀኝ የቆሙ ሁለት ጕልማሶች
ነበሩ ፡፡ የንጉሡ መልክ ቁመቱ መካከለኛ ፤ ዕድሜው ፳፫ ዓመት ጥቁር ሳይሆን ፈካ
ያለ ቀለም (የቀይ ዳማ) ያለው ፤ ፊቱ ክብ ፤ አፍንጫው ረዥም ፤ አገጩ ጢም ማብ
ቀል የዠመረ ነው ፡፡ ምንም ወጣት ቢሆን በሁኔታው የባለሥልጣንና የጌትነት
ሁኔታ ይታይበት ነበር»

ይኸንንም የመልካቸውን ዝርዝር የዕድሜያቸውን መጠን ከዚህ በፊት የካስ
ታንሄዳን መጽሐፍ መሠረት ያደረግነው ከአሁኑ ከአልቫሬዝ መጽሐፍ ጋር መስ
ማማቱን እንመለከታለን ፡፡ በካስታንሄዳ መጽሐፍ ላይ ''መጋረጃው ሲገለጥና
ንጉሠ ነገሥቱ ሲታይ ሮድሪግ በቀኝ እጁ መሬት ነክቶ ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ
ነሣ ፡፡ ከዚያም ንጉሡ በዓቃቤው ሰዓት አማካይነት ጤንነቱንና በዚህ አገር ኑሮው
መደሰቱን ቢጠይቀው ሮድሪግ ጤንነቱ ፍጹም ደህና ነው ፤ በክርስቲያን አገር በመ
ገኘቴና የመዠመሪያ የፖርቱጋል መንግሥት አምባሳደር ሆኜ ለመምጣት በመ
ቻሌ ደስ ብሎኛል'' ያለውን አልቫሬዝ ከመዝለሉ በቀር የሁለቱም ጸሐፊዎች አገላ
ለጥ ተመሳሳይ ነው ፡፡

በተረፈ አልቫሬዝ ስለደብዳቤው አቀራረብ እንደዚህ ሲል አተራረኩን ይቀጥ
ላል ፡፡ «እኛ በቆምንበትና ንጉሡ በተቀመጠበት ዙፋን መካከል ያለው ርቀት
የሁለት ጦር ርዝማኔ ስለነበረ . . . . . በኛና በንጉሡ መካከል ሆኖ መልእክቱን
ያመላልስ የነበረው ዓቃቤ ሰዓቱ ነበር . . . . . የመልክት መለዋወጡ ጉዳይ ከአ
ለቀ በኋላ በአገሩ ፊደልና ቋንቋ የተተረጐመለትን የጠቅላይ ገዥውን የደብዳቤ
መልእክት በዓቃቤ ሰዓቱ አማካይነት አምባሳደሩ (ሮድሪግ) አቀረበለትና አነበ
በው . . . . . . ከዚያ አንዳንድ የጥያቄና የመልስ መለዋወጥ ከተደረገ በኋላ አባቶቹ
ያሳዩትን . . . . . ስላየ እግዚአብሔርን አመስግኖ የጋራ ጠላቶቻችን (ቱርኮችና
ዓረቦች) በምጥዋና በሱዋኪም እየተዋጉ ስለሚያስፈሩ የፖርቱጋል ንጉሥ በነዚህ
በተባሉት ቦታዎች ላይ ምሽግ እንዲሠራ ቢያዝ . . . በዚያ ለሚቀመጡት ወታደ
ሮች ስንቅ የሚችል መሆኑን ገለጸ ፡፡ ደግሞ የዘይላ ወደብ ለአደን ለጂዳና ለሜካ
ብም ስለሚገኝበት ከሁሉ በፊት ዘይላን መያዝ አስፈላጊ መሆኑን አስገነዘበን . . .
እኛም ለዚህ መልስ የፖርቱጋል መርከብ ባለፈበት ሁሉ የሚኖሩ (ቱርኮችና ዓረ
ቦች) ሁሉ በፍርሃት ከተማቸውን እየጣሉ ስለሚሸሹ ሌሎቹንም ቦታዎች ለመያዝ
አያስቸግርም . . . . . ብለን አሳብ ለአሳብ ስንለዋወጥ ከቆየን በኋላ በአቀባበሉና
በአየነው ነገር ተደስተን ተለያየን» (1) ፡፡

በዚህ ዓይነት የመዠመሪያዎቹ የቅርታ ሳምንቶች አልፈው መልካም የመግ
ባባትና የመስማማት መንፈስ በሁለቱም ወገን ተፈጠረ ማለት ነው ፡፡ ንጉሡ ነገ

(1) Verdadeira ምዕ. 83

JSIC

ISIC

ISIC

ሥቱ ለፖርቱጋሎቹ ሽልማትም ስጦታም ድርጎም በየቀኑ እያሰጡ አስደሰቷቸው። በተለይም የቤተ ክህነቱን ሰው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን ብዙ ጊዜ ለብቻው እየጠሩ ስለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን እድ ርጋ ስለምታከብራቸው ስለአባ ዠሮም ፤ ስለ አባ ዶሚኒክና ስለ አባ ፍራንስ ፤ ስለገድላቸውም በዝርዝር እየጠየቁ ሲነጋገሩበት ሰነበቱ ። እርሱም ለሁሉም መልስ እየሰጠ ካስረዳቸው በኋላ ከጓደኞቹ ጋር ቅዳሴ የሚቀድሱበትና ጸሎት የሚያደርስ በት ከማኅፉዝ ጦርነት የተማረከ አንድ ትልቅ ባለቀለም ድንኳን ሰጥተው አስደሰ ቱት (1) ።

## ምዕራፍ ፳፩
## መስተንግዶው የቀዘቀዘበት ልዩ ልዩ ምክንያት

ምንም እንኳን በዚህ ባለፈው ዓይነት ወደ መጨረሻ ስምምነት ቢደርሱ ለመጡት እንግዶች ከመዠመሪያው ላይ ይኸን የመሰለ የቀዘቀዘ አቀባበል የተደረገበት ምክ ንያት ለዛሬ አንባቢና ሕዝብ ግር እንደሚለው የታወቀ ነው ።

የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ መንግሥት ያለበትን ሥፍራና ትክክለኛ ሁኔታ ለማግኘት የደከመ የፖርቱጋል ንጉሥ ቢሆንም በበኩሉ ዝምድናውን በጥብቅ የፈ ለገው የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ። ወይም የቱርክን ቁሳራዊ ኃይል በመሥጋት ሁለቱም በወዳጅነት ተባብረው ለመረዳዳት ተፈላልገዋል ቢባል ትክክለኛ ግምት ከመሆን አይዘልም ። የፖርቱጋል መንግሥት የኢትዮጵያን መልእክተኛ ማቴዎስን በክብር ተቀብሎ እንደ አንድ መስፍን አስተናግዶ ሲመልሰው ዶም ሮድሪግ የታላቁ የፖርቱጋል ንጉሥና የሕንድ አገረ ገዥ ዋና መላክተኛ (አምባሳ ዶር) ሆኖ ለመዠመሪያ ጊዜ ከዚህ በፊት ወደ አልታወቀው ወደ ክርስቲያን አገር ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ሲመጣ ማቴዎስ በሊስቦን እንዳገኘው ያለ ከፍ ያለ የክብር አቀባበልና የጉዞውን ችግር ሁሉ የሚያስረሳ መስተንግዶ አገኛለሁ ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው ። በደባርዋ ባሕር ነጋሽ ዶሪ ጓዛቸውንና ለንጉሡ የሚ ሰጠውን ገጸ በረከት መጫኛ አጋሠሥ አልሰጥም ብሎ ደጅ ያስጠናቸው አንሶ አሁን ደግሞ በቤተ መንግሥቱ እነሆ ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው ያልጠበቀው ነገር ደረሰበት ።

ይኸንኑ አቀባበል በዝርዝር የጻፈው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ እንደሚለው እን ግዶቹ ከመጡበት ቀን ዠምሮ ወር ሙሉ በጊዜውም ያለጊዜውም ከእንቅልፋቸው እየተቀሰቀሱ እየተጠሩ ተነሡ ፤ ተቀመጡ ፤ እለፉ ፤ እዚህ ቁሙ ፤ ከወዴት መጣ ችሁ ፤ ምን ትፈልጋላችሁ ፤ እየተባሉ እንደ ተራና እንዳልታወቀ ሰው ሲጠየቁ ፤ በዚህም ላይ የያዛችሁትን ገጸ በረከት ለዓቃቤ ሰዓት አስረክቡ ፤ አስቀድሞ የሰይፍ

(1) ምዕ. 84-85

ለጥ ፊቱ በሙሉ ይታይ ነበር . . . . ሰፋፊ የሆነ የሐር ሸሚዞች ለብሶ በዚያ ላይ ካባ ደርቧል ። ከታችም እግሩ በሙሉ ስለተሸፈነ አይታይም ። መስቀል ይዞ ከቆመው የእልፍኝ አሽከር በቀር ጐራዴ ይዘው ከዙፋኑ ግራና ቀኝ የቆሙ ሁለት ጐልማሶች ነበሩ ። የንጉሡ መልክ ቁመቱ መካከለኛ ፣ ዕድሜው ፳፫ ዓመት ጥቁር ሳይሆን ፈካ ያለ ቀለም (የቀይ ዳማ) ያለው ፣ ፊቱ ክብ ፣ አፍንጫው ረዥም ፣ አገጩ ጢም ማብቀል የጀመረ ነው ። ምንም ወጣት ቢሆን በሁኔታው የባለሥልጣንና የጌትነት ሁኔታ ይታይበት ነበር»

ይኸንንም የመልካቸውን ዝርዝር የዕድሜያቸውን መጠን ከዚህ በፊት የካስታንሄዳን መጽሐፍ መሠረት ያደረግነው ከአሁኑ ከአልቫሬጽ መጽሐፍ ጋር መስማማቱን እንመለከታለን ። በካስታንሄዳ መጽሐፍ ላይ "መጋረጃው ሲገለጥና ንጉሡ ነገሥቱ ሲታይ ሮድሪግ በቀኝ እጁ መሬት ነክቶ ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ ነሣ ። ከዚያም ንጉሡ በዓቃቤው ሰዓት አማካይነት ጤንነቱንና በዚህ አገር ኑሮው መደሰቱን ቢጠይቀው ሮድሪግ ጤንነቴ ፍጹም ደህና ነው ፤ በክርስቲያን አገር በመገኘቴና የመጀመሪያ የፖርቱጋል መንግሥት አምባሳደር ሆኜ ለመምጣት በመቻሌ ደስ ብሎኛል" ያለውን አልቫሬጽ ከመዝለሉ በቀር የሁለቱም ጸሐፊዎች አገላለጥ ተመሳሳይ ነው ።

በተረፈ አልቫሬጽ ስለደብዳቤው አቀራረብ እንደዚህ ሲል አተራረኩን ይቀጥላል ። «እኛ በቆምንበትና ንጉሡ በተቀመጠበት ዙፋን መካከል ያለው ርቀት የሁለት ጦር ርዝማኔ ስለነበረ . . . . . በኛና በንጉሡ መካከል ሆኖ መልእክቱን ያመላልስ የነበረው ዓቃቤ ሰዓቱ ነበር . . . . . የመልክት መለዋወጡ ጉዳይ ከአለቀ በኋላ በአገሩ ፊደልና ቋንቋ የተተረጐመለትን የጠቅላይ ገዥውን የደብዳቤ መልእክት በዓቃቤ ሰዓቱ አማካይነት አምባሳደሩ (ሮድሪግ) አቀረበለትና አነበበው . . . . . . ከዚያ አንዳንድ የጥያቄና የመልስ መለዋወጥ ከተደረገ በኋላ አባቶቹ ያላዩትን . . . . . ስላየ እግዚአብሔርን አመስግኖ የጋራ ጠላቶቻችን (ቱርኮችና ዓረቦች) በምቀኝና በሱዋኪም እየተዋጉ ስለሚያስፈሩ የፖርቱጋል ንጉሥ በነዚህ በተባሉት በታዎች ላይ ምሽግ እንዲሠራ ቢያዝ . . . በዚያ ለሚቀመጡት ወታደሮች ስንቅ የሚችል መሆኑን ገለጸ ። ደግሞ የዘይላ ወደብ ለአደን ለጂዳና ለሜካ እስከ ካይሮ ድረስ ለመላው የዓረብ አገር ለሚላከው ምግብ መተላለፊያና ብዙ ምግብም ስለሚገኝበት ከሁሉ በፊት ዘይላን መያዝ አስፈላጊ መሆኑን አስገነዘበን . . . እኛም ለዚህ መልስ የፖርቱጋል መርከብ ባለፈበት ሁሉ የሚኖሩ (ቱርኮችና ዓረቦች) ሁሉ በፍርሃት ከተማቸውን እየጣሉ ስለሚሸሹ ሌሎቹንም በታዎች ለመያዝ አያስቸግርም . . . . . ብለን አሳብ ለአሳብ ስንለዋወጥ ከቆየን በኋላ በአቀባበሉና በአየነው ነገር ተደስተን ተለያየን» (1) ።

በዚህ ዓይነት የመጀመሪያዎቹ የቅርታ ሳምንቶች አልፈው መልካም የመግባባትና የመስማማት መንፈስ በሁለቱም ወገን ተፈጠረ ማለት ነው ። ንጉሡ ነገ

(1) Verdadeira ምዕ. 83



ዓፄ ልብነ ድንግል በ፳፫ ዓመት ዕድሜያቸው ተስለው ሥዕሉ በፍሎራንስ ሲቀመጥ ዋናው ስለጠፋ ከዋናው ላይ ቀደም ብሎ የተገለበጠ (ረናቶ ለፌቨር)

ውጊያችሁን አሳዩ ፥ ከናንተና ከቱርኮች በጉብዝና ማን ይበልጣል ሲባሉና ከብርድ ላይ እየቆሙ ከተጉላሉ በኋላ በመጨረሻ ከመልክተኛና ከዓቀቤ ሰዓቱ ጋር ብቻ በመነጋገር ንጉሡን መገናኘት ተነፍገው ወደ ሠፈራችሁ ተመለሱ ሲባሉ በርግጥ ከመገረም ጋር ማዘን እንደሚገባቸው የታወቀ ነው ። እነዚህም እንግዶች የሕንዱ ጠቅላይ ገዢአቸው ዲዬጎ ሎፔዝ ምጥዋ ከባሕር ነጋሽ ዶሪ ጋር እንገናኘቷቸው ወደ ሕንድ ከተመለሰ ወዲህ ቀደም ብሎ በራሱ በባሕር ነጋሹ መስተንግዶ የገጠማ ቸው ጉድለት አሁን ደግሞ በንጉሡ ነገሥቱ አደባባይ ምንም ዓይነት የአቀባበል ውርደት ቢገጥማቸው በትዕግሥት ከመሸከም በቀር ሌላ ምርጫና ማኩረፊያ የላቸ ውም ።

ይህ መስተንግዶ ከቀዘቀዘበት ምክንያቶች አንዱ የገጸ በረከቱ ማነስ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ነገር ግን ከዚሁ ምክንያት ጋር የተያያዙ ሌሎችም ምክንያቶች አይጠፉም ። ከብዙዎቹ ምክንያቶች ዋነኛ ሆነው ሊቆጠሩ የሚችሉት ፤

፩ኛ. መላክተኛ ሆኖ ሊሰቦን የሄደውና መላክተኞቹን እየመራ የመጣው የጉዳዩን ቁም ነገረኝነት በዝርዝር ማወቅ ብቻ ሳይሆን ሊመዝንና ሊያስረዳም ይችል የነበረው ማቴዎስ ሲመለስ ደብረ ቢዘን ሞቶ ስለተቀበረና በዚህ ጊዜ ስለ ሌለ ።

፪ኛ. የጉዳዩ ወጣኝና አሳቢ ታላቂቱ ንግሥት እሌኒ (ያሄ በእደ ማርያም ባለ ቤት) ምንም በሕይወት ቢኖሩ ከሥልጣን ውጭ በመሆናቸው ነው ። ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ እንግዶቹ ዓፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት በደረሱበት ጊዜ እቴጌ ይቱ በሕይወት መኖራቸውን በምዕራፍ ፩፻ ከጠቀሰ በኋላ መሞታቸውን በ፫፻፳ ምዕራፍ ላይ ገልጿል ።

ISIC

ስለዚህ በዓፄ ልብነ ድንግል የወጣትነት ጊዜ ሙሉ የሞግዚትነት ሥልጣን የነበራቸው እቴጌ እሌኒ በዚህ ጊዜ እርጅናም ድካምም ተጭኗቸው ከሥልጣን ውጭ በጾም በጸሎት ተጠምደው አብዛኛውን ጊዜያቸውን በግዛታቸው በጉጃምና ባሠሩት በመርጡለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚቀመጡ ይመስላል ። በርሳቸው ፈንታ ባሁኑ ሰዓት የቤት ባለሥልጣኖች የንጉሠ ነገሥቱ እናት እቴጌ ናዖድ ሞገ ሳና ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል ናቸው ። በዚህም ላይ በአልቫሬጽ መጽሐፍ ላይ ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ምክንያቱን ሳይገልጡ ማቴዎስን ወዳጃቸውም ቢሆን ሐሰትን ይዞ የተጓዘ ነው በሚል ቃል ሐሰተኛ አድርገውታል (1) ። ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ በገጸ በረከቱ ማነስ ከሮድሪግ ጋር ንግግር በሚለዋወጡበት ጊዜ እንግዲያው ማቴዎስ ነው ያበለው የሚል ቃል ወርውረዋል (2) ። ይኸውም ማለት ማቴዎስ ከመሄዱ በፊት ወይም ሄዶ ከተመለሰ በኋላ ከምጥዋ ብዙ ገጸ በረከት እንደሚደር ሳቸው ልኮባቸው ነበር ማለት ነው ።

(1) VER.... ምዕ. 103
(2) " " 96

የእቴጌ እሌኒን በዚህ ሰዓት ከሥልጣን ውጭ መሆን በተገነዘብንበት ሰዓት ማቴዎስ በደብረ ቢዘን ሞቶ ከመቀበሩ በፊት ዕቃዬን በሙሉ ለንግሥት እሌኒ ስጡልኝ ብሎ ተናዞ ሞርአል (1) ። ስለዚህ ቀድሞውኑ ዓፄ ልብነ ድንግልና ጳጳሱ ወዳንድ ወገን ንግሥት እሌኒና ማቴዎስ በሌላ ወገን ሆነው ጐራ የለዩና በፖለቲካና ባስተዳደር በአሳብ በመለያየት ውስጠ ስምምነት ያልነበራቸው ይመስላል ። ስለዚህ አሁን ማቴዎስ ሞቶ ንግሥቲቱ ከሥልጣን ውጭ ሆነው ሳሉ በነርሱ እሳብና ጥረት ለመጡት እንግዶች መልካም መስተንግዶና አቀባበል ማድረጉ ለጊዜው አስፈላጊ መስሎ አልታያቸውም ይሆናል ።

፫ኛ. በጽሑፉ ላይ እንደተገለጸው ፖርቱጋሎቹ ብዙ ዓይነት ገጸ በረከትና የበረከተ የጦር መሣሪያ ያመጣሉ ተብሎ በተስፋ ይጠበቅ ኖሮ መሣሪያውና ገጸ በረከቱ መላክተኛው እንዳስረዳው በአስቸጋሪው የባሕርና የየብስ ጉዞ በየምክንያቱ የባከነውን በቂ ምክንያት አድርገው የኛዎቹ አልቆጠሩላቸውም ማለት ነው ። ንጉሡ አፄ ልብነ ድንግል የፖርቱጋል ንጉሥ የላከልኝን ገጸ በረከት ለምን አትስጡኝም ብለው የልፍኝ አሽከር መላካቸውን አልቫሬጽ ሲያመለክት በትክክል በዚህ ረገድ በንጉሡ ዘንድ ቅርታ እንደገባ ያስረዳል ።

፬ኛ. እነዚህ የመጡት መላክተኞች በኛ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ርኩስ ተኵላ መሳጢ የሚባለው የልዮን (ትልቁ ልዮን ፬፻፵ - ፬፻፷፩) ወገኖች ካቶሊኮች ያሁኑም ሊቀ ጳጳሳቸው ስሙ ያው ልዮን (ልዮን ፲ኛ ፲፭፻፲፫ - ፲፭፻፳፩) በመሆኑ የሁለት ባሕርይ ወገኖች ናቸውና ልንቀበላቸው ወይም መልካም አቀባበል ልናደርግላቸው አይገባም የሚሉ ለሃይማኖቱ እንጂ ለዝምድናውና ለፖለቲካው ግንኙነት ግምት አይሰጡ የቤተ ክህነት ወገኖች ተቃውመውም እንደሆነ አይታወቅም (2) ።
ISJC
የማይሰጡ የቤተ ክህነት ወገኖች ተቃውመውም እንደሆነ አይታወቅም (2) ።

፭ኛ. ወይስ እነዚህ የፖርቱጋል ተወላጆች ምንም ክርስቲያኖች ቢሆኑ አገራቸው ፖርቱጋል ፤ ግዛታቸው ሕንድ ከኢትዮጵያ የራቀ በመሆኑ እነሱን በፍቅር ተቀብለን ስናስተናግድ ወሬውን የቱርክ ሡልጣን ሰምቶ በቅርባችን ያሉት ግብፆችና የዘቢድ ፓሻዎች ተቀይመው በውስጣችን ያለውን የእስላም ተወላጅ ቀስቅሰው የጦርነት ፍዳ ሊያደርሱብን ይችላሉና አለመቀበሉ ወይም አቀባበሉን ማቀዝቀዙ ይሻላል የሚሉ የፖለቲካ ተመልካቾች ሹማምንት ተነሥተው ይሆን ? ።

ይህ እንደሆነ በርግጥ ቀጥሎ ባለው ጊዜ የግራኝ አህመድ እነሣሥ ከዚሁ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በዚህ አስተያየት አልተሳሳቱም ለማለት ይቻላል ። በኛ በኩል ስለዚህ ጉዳይ የሚናገር አንዳች የጽሑፍ ቅርስ ስለሌለ ከዚህ በላይ በመላ ጭምር ካቀረብናቸው አሳቦች የትኛው ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ችግር ነው ።

፮ኛ. በዚህ ላይ ደግሞ ዋናው የምናስታውሰው ከዚህ በፊት በውጭ አገር ጠላት የመሸነፍና የመገዛት ውርደት ቀምሶ የማያውቀው የኩሩው የኢትዮጵያ ቤተመንግሥት ልዩ ልዩ ወግ ፤ ስነ ሥርዓት የበዛበት ከዳዊት ፤ ከሰሎሞን ዘር የወረ

(1) Verdadeira .... ገጽ 92

(2) የዮሐንስ መደብር መጽሐፍ ዞተንበርግ ያሳተመው ክፍል 89 ገጽ 265-267 ። ሃይማኖተ አበው እመልእክተ ሲኖዲቆን ዘአቡነ ፊላታዎስ ተመልከት ፤

ደውና የተቀባው ንጉሠ ነገሥት ሰው እንዳያየው አንዳንድ ጊዜ በመጋረጃ ውስጥ የሚጓዘው የንጉሠ ነገሥቱም ከፍታና ርቀት ለውጭ አገር ሰውና መላከተኛ ለሸክም የሚከብድ መሆኑ አይካድም ። የዚህ ዓይነት አቀባበል ለውጭ ሰው እንግዳና ችግር ሲፈጥርበት በኛዎቹ ዘንድ አግባብና ሥርዓት ሆኖ ሊገመት ይችላል ። በሠለጠነውና ከውጭ አገር በመጣው ሰው ዘንድ እንኳን አንድ ወር አንድ ቀን እንኳን ደጅ መጥናት ያበሳጨዋል ። በኛዎቹ ዘንድ ግን ከተቀባው ንጉሥ ጋር ለመገናኘት ዓመት የረዘመ ደጅ ጥናት ቢገጥም እንደ ልማድ ተቆጥሮ ኀዘኑም ብስጭቱም የቀዘቀዘ ነው ።

ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ዓቃቤ ሰዓቱ ማን መሆናችንን እያወቀ ከወዴት መጥታችኋል ምን ትፈልጋላችሁ እያለ በመደጋገም ፫ ጊዜ እየጮኸ መጠየቅ ነበረበት ሲል ጠቅሷል ። ወደ ንጉሡም የቀረብን ጊዜ እየመሩ ይዘውን የሄዱት ሹማምንቶች ከበሩ ውጭ ሆነው «ጌታ ሆይ እምጣቸው ያሉኝን ፈረንጆች አመጣሁዋቸው» እያሉ በየተራ ከውጭ ሲጮሁ ከውስጥ ከንጉሡ ዘንድ «ግቡ» የሚል ድምፅ ይሰማ ነበር ያለው ከዚሁ ሥነ ሥርዓት ከተባለው ጋር የተያያዘ ነው። እንደዚሁም ምናልባት እነዚህን መልክተኞች እንደመጡ ምንም ደጅ ሳይጠኑ ከተቀባው ንጉሠ ነገሥት ጋር ማገናኘት ክብራቸውን ይቀንሳል የሚል ስሜትም በጭማሪ ኖሮ ትንሽ ደጅ ይጥኑ የሚሉ አሳብ እንዳለበት አይታወቅም ፤ በዚህም ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ፩ኛ ከአምስት ዓመት በፊት በማኅፉዝ ላይ ያገኙት ድል ፤ ፪ኛ በዚሁ መካከል ቱርኮችና ግብጾቹ ሲዋጉ ለርሳቸው የተመቸው የሰላም ጊዜ ኩራት አትርፎ እንግዶቹን ተቀብሎ ለማነጋገር አልቸኮሉበትም ይሆናል ።

ISIC

የኢትዮጵያ የዚያን ዘመን ነገሥታት የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሹማምንት ዓቃቤ ሰዓቱ ፥ ቢትወደዱ ፥ ራሱ ፥ ጽራግ ማሠሬው ፥ ጸሐፊ ላሙ ፥ ምንም እንኳን ባገሩ ትምህርት ሊቅነት ቢኖረው በተፈጥሮም ብልህነት ባያጣ ፥ ዝግንነቱም የታወቀ ቢሆን በጠቅላላው ካገሩ ያልወጣ ፥ የውጭን አገር ትምህርትና የቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓት የማያውቅ ስለሆነ ለጊዜ ውድነት ዋጋ መስጠት ይሳነው ይሆናል። በፈረንጅ አገር አንድ ሰው የአንድ ቀን ይቅርና የአንድ ሰዓት ጊዜ በከንቱ መጥፋት ያበሳጨዋል ። በኛ ዘንድ ግን እላይ እንዳልነው አንድ ሰው በተለይ ከንጉሠ ነገሥት ሊገናኝ የመጣ አንድ ወር ወይም ሁለት ወር ደጅ ቢጠና በተለይ ለዚያን ዘመን ባለሥልጣን አግባብ መስሎ ነው የሚታየው ። ጊዜም ወርቅ ነው የተባለው ፍልስፍና እንኳን ሊሠራበት ወሬው በዚያን ጊዜ መሰማቱ ያጠራጥራል ።

እነዚህ ያገራችን ልዩ ልዩ ባለሥልጣኖች ከውጭው አገር ኑሮና ሥነ ሥርዓት ከሥልጣኔውም ባለመተዋወቅ የተነሣ ከአሕዛብ ወገን አድርገው በሩቁ ለሚመለከቱት ለውጭ አገር ሰው ለፖለቲካውም ለችሎታውም ለድርጅቱም ለዕውቀቱም ግምት መስጠት ይሳናቸዋል ። በዚህ ምክንያት የራሳቸውን ንጉሠ ነገሥት የራሳቸውን አገር ትምህርትና ዕውቀት ሲያከብሩ ከዚያ ውጭ ለሆነው ግምትና ክብር መስጠት ያዳግታቸዋል ።

አንዳንድ የዋሃን ሊቃውንትና ነገሥታትም ዓለም ማለት ኢትዮጵያ ብቻ መሆ

ንዋን ደንበኛ ትምህርትም ቅኔና ዜማ የሚመስላቸው ነበሩ ። ለዚህም ማስረጃው ዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ራሳቸውን እንደ ዓለም ንጉሥ በመቁጠር ለውጭ አገር ነገሥታትና ጳጳሳት በጻፉበት ደብዳቤ እናት «መጽሐፈ መልእክት ዘንጉሠ ነገሥተ ዓለም አድያም ሰገድ» ብለዋል ። እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ የኢጋሚው ገዥ ደጃዝማች ሰባ ጋዲስ ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ለአባ ጴጥሮስ በጻፉት ደብዳቤ ግርጌ «ማኅተም ዘደጃችማች ሰባ ጋዲስ ንጉሠ ዓለም» ብለው ያተሙበት ደብዳቤ በሎንዶን መጻሕ ፍት ቤት ይገኛል (1) ።

ቀድሞ ግሪኮችና ሮማውያን የነርሱን ሃይማኖትና ዕውቀት ያልያዘውን ሕዝብ በድምሩ (BARBARE) አረመኔ ይሉት እንደነበረው የኛም አገር ሊቃውንት በተ ለይ ብዙ መጽሐፍ ያላነበቡት የውጭን አገር ሁኔታና ጥበብ ያላዩትና ያልሰሙት ክፍሎች ከኢትዮጵያና ከቊስጥንጥንያ ጳጳሳትና ክርስቲያን ነገሥታት ከእስክንድ ርያ ሊቃነ ጳጳሳት ውጭ ያለውን አረማውያን ፡ አሕዛብ ፡ ተንባላት መናፍቃን እያሉ ለሰውነታቸውም ለዕውቀታቸውም እምብዛም ዋጋ አይሰጡትም ነበር ። በኛ ዎቹ ዘንድ ይልቁንም በዚያን ሰዓት እንደ ዕውቀት ሆኖ የሚቆጠረው የብሉይና የሐዲስ የቄርሎስና የአፈ ወርቅን የመጻሕፍት ትርጓሜ ማወቅ ከዚያም በዛ ቢል ፍትሐ ነገሥት ፡ የዮሐንስ መደብር ፡ የጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ፡ (ጊዮርጊስ አቡን አል አሚድ) የአቡ ሻክር ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐሙትን መጻሕፍቶች ፡ የአ ክሱም ንቡረ ዕድ ይስሐቅና የደብረ ሊባኖስ እጨጌ እና አባ ዕንባቆም የተረጐሟ ቸው ሥጋዊና መንፈሳዊ መጻሕፍት ምርምር መሆኑን በዚያን ጊዜ ብዙ ጊዜ ባለሥ ልጣንም የሚሆነው እነዚህን ዕውቀቶች ያጠናቀቀ መሆኑን በምዕራፍ ፳ ላይ አት ተናል ።

እነ አልቫሬዝ በዚህ አቀባበል ጊዜ የመንግሥቱ ባለሥልጣን መነሾሴ እያሉ የሚጠሩት ዓቃቤ ሰዓቱን መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ንጉሡ ካሉበት ወጣ እያለ ከየት መጥታችኋል ምን ትፈልጋላችሁ እያለ ፫ ጊዜ ጠየቀን ያሉት ዓቃቤ ሰዓት ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ የነበረው አምሐ ጽዮን ወይም አምሐየስ አይመስ ልም ። ነገር ግን በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍና ባዔ ልብነ ድንግል ዜና መዋዕል ውስጥ ስሙ ተደጋግሞ የተጠቀሰውን ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስን ሳይሆን አይቀርም ። ይኸም ዓቃቤ ሰዓት ወደፊት በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዓባይ ዳር ከንጉሡ ጋር ሲሸሽ አብሳማ ኑር ንጉሡን ያገኘ መስሎት ማርኮ እንደገደለው እናነባለን ።

ያቃቤ ሰዓቱ ሥልጣን በዚህ ጊዜ ከፍ ያለ እንደነበረ ዜና መዋዕሉ ያስረዳል ። በፍርድ ጊዜ ከራስ ቢትወደድ ቀጥሎ ከንጉሠ ነገሥቱ በፊት ይፈርዳል ። የንጉሡ ባለሟልና አማካሪ ሲሆን በዚሁ ማዕረጉም መቀመጫውም ልብሱም ከሌሎቹ ከቢትወደዶቹ የበለጠ ነው ማለት ነው ። አልቫሬጽ በመጽሐፉ እንደበርናስ ሆኖ የተሰፋ ካባ ደርቦ ትልቅ የሐር ቆብ የጫነ የንጉሠ ነገሥቱ መምህርና ዘመድ የሚ ሉት ዓቃቤ ሰዓት በሚባል ማዕርግ የሚጠራው በአገሩ ውስጥ ሁለተኛ ባለሥልጣን ነው ያለው ትክክልና እርሱን ነው (2) ።

(1) Cataloque of the ethiopic manuscripts ገጽ 326

(2) Verdadeira .................. ምዕ. 70

ISIC

# ምዕራፍ ፳፱
## የንግሥት እሌኒ ከሥልጣን መውጣት

በሸዋ ከነበሩት ነገሥታት ካፄ ዓምደ ጽዮን ዠምሮ እፄ ዘርዓ ያዕቆብና እፄ በእደ ማርያም እፄ እስክንድርም ባንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ሚስቶች መያዛቸውን ተመልክተናል ። ይኸም አብዛኛው ጊዜ የሥጋ ፈቃዳቸውን ለማስደሰት ሳይሆን የፖለቲካ ጋብቻ በማስገደዱ ጭምር መሆኑን ፖለቲካውም ከእስላሞቹ ባላባቶች ጋር በጋብቻና በዝምድና ተሣሥሮ ሰላምንና ጸጥታን ባገር ላይ ለማረጋገጥ መሆኑን ይኸም ዘዴ ከጥንት ዠምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በሌላ ውም አገር የሚሠራበት መሆኑን በአለፈው አመልክተናል ።

በዚሁ መሠረት ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፍሬ ማርያምንና ጽዮን ሞገሳን ባገቡበት በዚያው ጊዜ የሐድያውን ገራድ የመሐመድን ልጅ በክርስትና አስጠምቀው ስማ ቸውን እሌኒ ስመ መንግሥታቸውን ዣን ዛላ (የዘይላ ንግሥት ?) እሰኙተው የቀኝ ባለቤት (ቀኝ ዕ በዓልቲሐት) ብለው እግብተዋቸው እንደነበረ ይኸንኑ የፖለቲካ መስመር ዓፄ በእደ ማርያምም ዓፄ እስክንድርም ዓፄ ናዖድም እንደተከተሉት ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚባለው መጽሐፍ ምዕራፍ ፴፩ ተጽፏልና አሁን በዚህ ምዕራፍ ስለ ዓፄ በዕደ ማርያም ባለቤት ስለንግሥት እሌኒ ብቻ ባጭሩ የተገኘውን ያህል እንጽፋለን ።

ISIC

አንድ በአማርኛ የተጻፈ ታሪክ «. . . . . በእደ ማርያም የእነሴይቱን ባላባት የምጣድ ቤቲቱን እሌኒን አግብቶ አነገሣት ይህቺም ንግሥት መርጡለ ማርያምን ሠራች» ይላል በሌላም ላይ እልፍ ብሎ የናዖድ እናት ያደርጋታል ። ታሪኩ በጥየቃ የተጻፈ ስለሆነ በሙሉ ሊታመን አይቻልም በርሳቸው ዘመን አቅራቢያ የነበሩ ፖርቱጋሎችና ሌሎችም ጸሐፊዎች ሁሉ የደዋሮው የመሐመድ ልጅ ያደርጓቸ ዋል (1) ። በግዛት የጐጃምን አብዛኛውን ክፍል ትገዛ እንደነበረ በእነሴ የሚገኘ ውን መርጡለ ማርያምን ያሠራች እርሷ መሆኑን ታሪክ ጸሐፊ ሁሉ ተስማምቶበ ታል ። ምናልባት አባት የደዋሮ ባላባት እናት ጐጃሜ ትሆን ይሆን አይታወቅም ።

ታሪክ ነገሥቱ ስለ ንግሥት እሌኒ ችሎታና አዋቂነት እንደዚህ ሲል የጻፈ ውን እዚህ ላይ ማስታወስ ይጠቅማል ። «. . . . . . እሌኒን ንጉሡ (በዕደ ማርያም) በጣም ወደዷት ፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ምጽዋትንና ቁርባንን የምት ፈጽም ሃይማኖትንና ምግባርን የተመላች ፍጹምት ስለሆነች ። በዚህ ዓለምም መጻሕፍትንና ንግግርን ፣ ሕግንና የማዕድን ሥርዓት የምታውቅ ስለሆነች ።

(1) ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ያፄ ልብነ ድንግል አጭር ታሪክ ንጉሡ በናታቸው በናዖድ ሞገሳና ይል
ቁንም በንግሥት እሌኒ ምክር መጠቀማቸውን በጠቀሰበት ላይ እንደዚህ ብሏል «. . . . . . . ወእ
ሜሃ ትትሜገብ መንግሥት በትእዛዘ ወላዲቱ ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ወበምክረ ካልእታ ንግ
ሥት እሌኒ እስመ የአምራ ሠሪአ ቤተ መንግሥት ወፈድፋደሰ ዛቲ ጠባብ እሌኒ ተአምር ሕገ
መንግሥት በታሪካ ሠለስቱ ነገሥት (በእደ ማርያም ፣ እስክንድር ፣ ናዖድ)» የልብነ ድንግል
ታሪክ ገጽ 6 በድጋሚ የተጠቀሰ ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ንግሥት እሌኒን እንደናታቸው አደረጓት (1) ።

ስለዚህ እኝህ ንግሥት በጐንደር መንግሥት እንደ አፄ በካፋ ባለቤት እንደ እቴጌ ምንትዋብ ፤ እንደ አፄ ምኒልክ ባለቤት እንደ እቴጌ ጣይቱ ያሉ ብልህ አዋቂ ታላቅ ንግሥት ኖረዋል ። ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ንግሥት እሌኒ የጐጃምን አብዛኛውን ክፍል ትገዛ ነበር ሲል ጠቅሷል (2) ።

የሆነ ሆኖ እኚህ ታላቅ እመቤት ያፄ በዕደ ማርያምን ያፄ እስክንድርንና ያፄ ናዖድን ዘመነ መንግሥት አርባ ዓመት ያህል ሲያንስም ሲበዛም በሥልጣን አሳልፈው እንደዚሁም ያፄ ልብነ ድንግልን የመዠመሪያውን አሥር ዓመት ያህል ዘመነ መንግሥት አዳርሰው በአሁኑ ጊዜ በቤተ መንግሥቱ መኖራቸውን ፤ ከዚያ በመጨረሻ ወደ መርጡለ ማርያም ሄደው ሳሉ መሞታቸውን በርሳቸው ሞት ባለሥልጣኑ ሁሉ ኀዘን እንደገባው አልቫሬጽ ገልጿል (3) ።

በመጨረሻ ጊዜ ከሥልጣን የራቁት ከልባቸው በመነጨ መንፈሳዊ ምኞትና የመጨረሻ ጊዜ ዕድሜያቸውን በምንኩስና ፤ በጸሎት ለማሳለፍ ይሁን ፤ ወይም በዕድሜ በገፉ ሞግዚትና ለግዛት በደረሰ ወጣት ነጋሢ መካከል የሚደርሰው የተለመደ የሥልጣን መፋለምና ሺሚያ በርሳቸውና ባፄ ልብነ ድንግል መካከል ደርሶ ወጣቱ ልብነ ድንግል የመንግሥቱን ሥልጣን እንደ አባቶቻቸው በሙሉ መያዝ ወይም የንግሥት እሌኒን ሥልጣን ወደ እናታቸው [illegible]ናየድ ሞገሳ ማሳለፍ ስለፈለጉ በዚሁ ያያታቸውን ያፄ በዕደ ማርያምን ባለቤት አስቀይመው ዓለም በቃኝ አሰኝተዋቸው እንደሆነ አይታወቅም ።

ነገር ግን ወደፊት አፄ ልብነ ድንግል በዶም ሮድሪግና በአልቫሬጽ መሪነት የመጡትን ፖርቱጊዞች በመጡ በ፯ኛው ዓመት መልሰው ሲልኩ ራሳቸው በቀጥታ ለፖርቱጋሉ ንጉሥ ለአማኑኤል በጻፉት ደብዳቤ ላይ ዘውድ ጭኜ የነገሥሁ ጊዜ ዕድሜዬ ገና ፲፩ ዓመት ነበር ። ስለዚህም መንግሥቴ ይመራ የነበረው እንደ እናቴ በምመለከታት በንግሥት እሌኒ እጅ ነበር ፤ ሲሉ ገልጸዋል ። በዚህ አጻጻፍ ሁለቱ በፍቅርና በሰላም የተለያዩ ይመስላል ። በማረጋገጥ ፈንታ ይመስላል የሚል ቃል ያስጨመረን ምንም እንኳን በዚህ ደብዳቤ ንጉሡ እንደ እናቴ በምመለከታት የሚል ቃል ቢጠቅሱ በፍጹም ፍቅር መለያየታቸውን አያስረዳም ። በታሪካችን ውስጥ በሥልጣን ፈለግ ባፄ ሚናስና በናታቸው በሰብለ ወንጌል ፤ በአፄ ኢያሱ አድያም ሰገድና በልጃቸው በተክለ ሃይማኖት ፤ በእቴጌ ምንትዋብና በልጅ ልጃቸው ባፄ ኢዮአስ መካከል ከደረሰው ጠብና ክርክር በቀር በቅርቡ ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ በእቴጌ ጣይቱና በወጣቱ ነጋሢ በልጅ ኢያሱ መካ

(1) ወለቀኝ ባልቲሐት ዘሰማ እሌኒ አፍቀራ ጥቀ ንጉሥ በጽታሃ እስመ ኮነት ፍጽምተ በኵሉ ኀበ እግዚአብሔር በገቢረ ጽድቅ ወሃይማኖት በገቢረ ጸሎት ወቁርባን ። ወበዓለምኒ በሥርዓተ ማዕድ ወሕግ በአእምሮ መጽሐፍ ወነገር ። በእንተዝ ኵሉ አፍቀራ ንጉሥ ፈድፋደ ለንግሥት እሌኒ ወረሰያ ከመ እሙ ። ያፄ ዘርዓ ያዕቆብና ያፄ በዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ፔሩሾን የተረጐመው ገጽ 175 - 176

(2) አልቫሬጽ ምዕ. 118

(3) አልቫሬጽ ምዕ. 120

ከል የሥልጣን ሽሚያ ሲፈጠር መኳንንቱ እንፌታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እቴጌ ጣይቱን ከሥልጣን ማስወጣታቸውና እንጦጦ ማርያም ሄደው በሰላም እንዲቀመጡ ማስገደዳቸው ሳይቀር በሌላው ግንኙነት ግን እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ መሳፍንቱና መኳንንቱ እቴጌ ጣይቱን በግልም በጉባኤ ንግግርም እናታችን እመቤታችን ሲሉዋቸው ኖረዋል ።

በዚህ ላይ አፄ ልብነ ድንግል ለሥልጣን ሲደርሱ ከርሳቸው በቀር በርሳቸው ዙሪያ ያሉት እናታቸው እሌኒ ያፄ ናዖድ ባለቤት (ናዖድ ሞገሳ) ወይም የራሳቸው ባለቤት እቴጌ ሰብለ ወንጌል አሁን የሥልጣኑ ተራ የኛ ነው ።እርሳቸው ብዙ ዘመን ስለገዙ ይብቃቸው መርጡለ ማርያም ሄደው ይቀመጡ ለማለት አይመስሉም ።

ይሁን እንጂ እኝህ ንግሥት እላይ እንዳልነው የሦስት ነገሥታት ገዜ (፵ ዓመት) አሳልፈው ካፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት አሥር ዓመት ያህል ሠርተው እንደሆነ በድምሩ ፶ ዓመት በሥልጣን ቆይተዋል ማለት ነው ። በዕድ ማርያ ምንም ሲያገቡ ዕድሚያቸው ወደ ፳ ዓመት ግድም እንደሆነ ባሁኑ ጊዜ ጠቅላላ ዕድሚያቸው ወደ ሰባ መድረሱ ነው ።

ነገር ግን በማናቸውም ረገድ ንግሥት እሌኒ ማቴዎስን ልከው በወጠኑት ወዳጅነት ምክንያት ያፄ ልብነ ድንግል መንግሥት በግራኝ አህመድ አጥቂነት ከተገለበጠ ወዲህ ፬፻ የፖርቱጋል ወታደሮች ከሕንድ በክርስቶፎሮስ ደጋማ መሪነት መጥተው በነርሱ እርዳታ ገላውዴዎስ መንግሥታቸውን ስላቋቋሙ ክርስቲያናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት የኝህ ታላቅ ንግሥት የእሌኒ ባለውለታ መሆን አለበት ። በይፋት ፤ ወይም በጐጃም በእነሴ ተማሪ ቤት የኢትዮጵያ መንግሥት ቢሠራ አደባባይና መንገድ ቢከፈት አንዱን ዋነኛውን በርሳቸው ስም መሠየም ፤ ሁለተኛውን ዝቅ ያለውን ለአርመናዊው ለማቴዎስ ስም መስጠት አግባብ ነው ። ላገር ሠርተው የሞቱትን ሁሉ ታሪካቸውና ስማቸው ተቀብሮ እንዳይቀር ልንቀሰቅሰው ይገባናል ። ለዚህም ኢትዮጵያ ዘር ሳትለይ በጎ ተግባርና ቅን አገልግሎት ላደረገላት ሁሉ ውለታ የማታስቀር መሆኗን በዓለም ፊት ያረጋግጣል ።

## ምዕራፍ ፳፫
## የኢትዮጵያና የፖርቱጋል የተያያዘና የተለያየ ጥቅም ።

ባለፈው ምዕራፍ ከፖርቱጋል ንጉሥ ታዞ የሕንድ አገረ ገዥ ምጥዋ ድረስ በመርከብ ያመጣቸው መላክተኞች በምን አኳኋን ወደ አፄ ልብነ ድንግል እንደደረሱ ከደረሱ በኋላ የደረሰባቸውን ችግር ፤ ችግሩም ሊደርስ የቻለበትን ምክንያት ተመልክተናል ።

ይሁን እንጂ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው የተያያዘ ጥቅም ሁለቱንም ሊያለያያቸው አይችልም ። የፖርቱጋል መልክተኞች መሪ ዶም ሮድሪግ ከንጉሡ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ከተገናኘ ወዲህ ሁለቱም ወገኖች የመዠመሪያውን ቅርታና

ክርክር እያየር ሠርዘው ወደ መቀራረብና ወደ መወዳጀት ደረሱ ። ሁለቱም ወገ
ኖች የየግል ጉዳያቸውን ተገላልጠው ሲነጋገሩ የሁለቱም ጉዳይ ርስ በርስ የተያያዘ
መሆኑን ወደ መረዳትና በመካከሉ ቅር የሚያሰኝ ነገር ቢገኖምም ቅርታቸውን ሁለ
ቱም በትዕግሥት እያሳለፉ ወደፊት ጥቅማቸው የሚከናወንበትን አሳብ ያደራጁ
ዠመር ። የፖርቱጋል መንግሥት ጉዳይ ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን መንግሥት
መሣሪያ አድርጎ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያለውን የዘይላንና የምጥዋን ወደቦች ከግብፆ
ችና በቅርብ ጊዜ (፲፭፻፲፯ እ.ኤ.አ.) ግብፅን ከያዙት ከቱርኮቹ እየተሻማ ለመያዝ
ነው ። በነዚህ አውራጃ የሚገኙትን እስላሞች በኢትዮጵያ ያሉትን በተዋሕዶ ክር
ስትና የሚያምኑትን ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመሳብ ምኞት ስላለ የሮማ
ሊቀ ጳጳስና መላክተኞቻቸው ሰፊውን የፖርቱጋል መንግሥት ድል አድራጊነትና
ግዛት እየተከተሉ የካቶሊክን ሃይማኖት በሰፊው ለመዘርጋት ንጉሡና ሊቀ ጳጳሳቱ
ኅብረት አድርገው እንደነበረ የታወቀ ነው ። የካቶሊክ ንጉሥ ሥልጣንና ግዛት
ባለፈበት የሮማ ቤተ ክርስቲያን የመስፋፋትና የመደርጀት ጥቅም ስለምታገኝ
ኟቱ መሪዎች ሁልጊዜ በኅብረት ይሠራሉ ።

የኢትዮጵያ ጉዳይ ደግሞ አገር በተለይ የክርስቲያን ነክ የሆነውን ቆርጠው
ሳይሰጡ ተዋሕዶ ሃይማኖትም እንደከበረ ከሥፍራው ሳይነቃነቅ ከፖርቱጋል መን
ግሥት ጋር በክርስቲያን ወንድማማችነት በጥቅምና በወዳጅነት ብቻ ተሳስሮ በደ
ቡብ ኢትዮጵያና በምሥራቅ በኩል ያሉትን በየጊዜው እየሸፈቱ አንገዛም የሚሉ
ትን ሲመቻቸውም እስከ ደፋት እስከ ደዋሮ ድረስ እየወጡ አገር የሚዘርፉትን የአ
ዳልንና የሱማሌን ባላባቶች እየደመሰሱ ለማሳመን ፤ ከዚያም የሚቻል ሲሆን የነር
ሱን ደጋፊ የቱርክን መንግሥት ማጥፋትና ኢየሩሳሌምን ይዥም ባይቻል በር የሆኑ
ትን የምጥዋን ፤ የዘይላን በር አስለቅቆ ነፃ አውጥቶ ሊሳለሙም ሊነግዱም ወደ ቅድ
ስት ሀገር የሚሄዱት ኢትዮጵያውያን ከኢየሩሳሌም ከሶርያም ወደ ኢትዮጵያ የሚመ
ጡት መነኮሳትና ሊቃውንት እንደልባቸው እንዲመላለሱ ነው ። በዚህም ላይ አፄ
ልብነ ድንግል በዘመኑ ያላቸውን የጦር ወታደር እንደ ፖርቱጋል ወታደር በደንብ
ለማሠልጠንና ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያና የእጅ ሥራ የሚያስተምሩ መምህራን
ከዚሁ መንግሥት ለማግኘት ምኞት እንዳላቸው ወደፊት ከሚጽፉት ደብዳቤ ላይ
እንገነዘባለን ።

ዳሩ ግን ቀድሞ ፖርቱጋሎች የኢትዮጵያንና የንጉሡዋን ወሬ በሩቅ ከመስ
ማት በቀር የዕውቀቷንና የሥልጣኔዋን ደረጃ ፤ የግዛትዋን ስፋት ፤ የወታደሩን ድር
ጅትና መጠን እንደማያውቁ ሁሉ እንደዚሁ አፄ ልብነ ድንግልና በዙሪያቸው
ያሉት ሹማምንት ወደ ፈረንጅ አገር ደርሰው የፖርቱጋልን መንግሥት ኃይልና
ድርጅት ስለአላጠኑትና ስለማያውቁት በንጉሡ ትእዛዝ ዓቃቤ ሰዓቱ (ነገደ ኢየሱ
ስን)ና የእልፍኝ አስከልካዩ አብዲናጎ የመልክተኞቹን ቍጥርና ስንቅ የጦር መሣ
ሪያ እንደያዙ በጠየቁበት ጊዜ ከፖርቱጋልና ከቱርክ በጦርነት ማን ይበልጣል ፤
ሁለቱስ ቢዋጉ ማን ያሸንፋል ፤ ለቱርኮቹና ለእስላሞቹስ የነፍጥ ሥራን ማን አስ
ተማራቸው እያሉ ሲጠይቁና ሲመረምሩ መሰንበታቸውን ባለፈው አንብበ

ናል (1) ። ይኸን ሁሉ ሌላውንም ጠቃሚ መረጃ ዝርዝር ወረውን ጭምር ሊያስረዳ ይችል የነበረው የራሳቸው መልክተኛ ማቴዎስ ሲመለስ ከመንገድ መሞቱ ጐድቷል ማለት ነው ።

ይኸንን የመሳሰለውን ጥያቄ እያቀረቡ ንጉሡ በመልክተኞቻቸው አማካይነት መመርመራቸው የዚህን የአውሮፓ ክርስቲያናዊ መንግሥት ጠቅላላ ኃይል አውቀው ከርሱ ጋር ለመዛመድ ኃይሉም ከቱርክ ጋር እየመጣጠን ወይም እይበልጥ እንደሆን እንግዲያውስ አያዋጣንም ብሎ ችላ ለማለት ያሰቡ ይመስላል ። ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ይኸን የመሰለ ምርመራ ሊያደርጉ የሚገባው ከፖርቱጋልና ከቱርክ ውጭ ከሆነ ከሌላ ከሦስተኛ ተመልካች ካልሆነ በቀር ምንም ቢሆን ራሱ ሲጠየቅ መንግሥቱ ወይም የመንግሥቴ ኃይል ከሌላው ያንሣል ብሎ የሚመልስ ሐቀኛ መላክተኛ እንደማይገኝ የታወቀ ነው ። እንደ እውነቱም የሆን እንደሆነ የቱርክና የፖርቱጋል ኃይል በአሁኑ ሰዓት ሊመጣጠን ይችላል ። ዳሩ ግን ልዩነቱ የቱርክ ግዛት መደዳውን በራሱ አገር ዙሪያ በመካከለኛው ምሥራቅ ከዚያም ተያይዞ እስከ አፍሪካ ሰሜንና ከዚያም እስከ ነምሳ የተስፋፋ ሲሆን የፖርቱጋል ግዛት በያለበት በእስያና በአፍሪካ በደቡብ አሜሪካ የተበታተነ ነው ። ለኢትዮጵያ የባላጋራዎቿ ደጋፊ የቱርክ ግዛት አካባቢዋ ሲሆን ለወዳጅነት ያሰበችው የፖርቱጋል አገር ከርሷ ይርቃል ችግሩም እዚህ ላይ ነው ። ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤቴ እንደሚባለ፴፮፻፶ይማኖት ልዩነት የፈጠረው ውዝግብ ሆኖ ነው እንጂ ዝምድናውም ሁሉም ከጐረቤት ጋር ባማረ ነበር ። ዳሩ ግን ጐረቤት ጠላት ሲሆን የሩቅ ዘመድ ከመፈለግ በቀር ሌላ መውጫ የለም ።

ስለዚህም ዓፄ ልብነ ድንግል የፖርቱጋል መንግሥት በሕንድ አገር በአፍሪካ ሰሜን በኮንጎ ያገኘውን ድል በቅርቡ በምጥዋ ያለውን የቱርክን ኃይል አጥፍቶ እነዚህን መላክተኞች ለመላክ መቻሉን ስለሰሙትና ስለሚያውቁት በፖርቱጋል ኃይል ለመተማመን ይበቃቸዋል ። ነገር ግን የዚህን መንግሥት ኃይል በሰሙበትጉን ደግሞ የቱርክ የኃይል መጠን ፈጽሞ ሊሠወራቸው አይችልም ። የቱርክ መንግሥት ባሁኑ ጊዜ መንግሥቱን ማጽናት ብቻ ሳይሆን ከቍስጥንጥንያ ብዙ ግዛት ቀምቶ የሜሶፖታሚያ የሶርያ ጌታ መሆኑ የኢትዮጵያን መልክተኞች እ. አ. ቆ. ፲፰፻፲፯ ዓ. ም. በውርደት የተቀበላቸውንና የመጣልኝ ገጸ በረከት ወራዳ ነው ብሎውን ሡልጣን ቱማንን በአደባባይ ሰቅሎ የግብፅና የአካባቢው ሁሉ ጌታ ጽኑ ገዥ መሆኑን መስማታቸውና ማወቃቸው አይጠረጠርም ።

በዚህ ምክንያት የሁለቱን መንግሥታት ኃያልነት እንደሰሙት ሁሉ የቱርክና የፖርቱጋል ወታደሮች ሲዋጉ ማን ያሸንፋል ብለው ሮድሪግን እስከ መጠየቅ የደረሱት ልዩነታቸውን በትክክል ለማወቅ ተቸግረው ይሆናል ። ሮድሪግ ግን በተጠየቀ ቁጥር ከፊተኛው ቀን መልስ ወዲህ በየጊዜው ያገሩን የጌታውን ገናንነት በምድርም በባሕርም ድል አድራጊ መሆኑን ከመናገር እርፍ አያውቅም ። እርሱ

(1) Verdadeira ምዕራፍ 76

ራሱ ሊከበር የሚችለው ጌታውን በማስከበር መሆኑ ሊዘነጋው አይችልም ።

የሆነ ሆኖ ሁለቱ ወገኖች ኢትዮጵያውያኖቹና ፖርቱጋሎቹ ሲመራመሩ ሲስ ላለሉ ስንብተው መደምደሚያውን ሁለቱም ክርስቲያኖች ስለሆኑ በቱርክና በእስ ላሞቹ ላይ በግድ ወደ መቀራረብና ወደ መስማማት ደርሰው በመጨረሻ መልክተ ኞቹን ንጉሡ ለመቀበል ወሰኑ ። ከተቀበሉዋቸውም በኋላ በሁለቱ መካከል የስም ምነት መንፈስ መፈጠሩን በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንረዳለን ።

## ምዕራፍ ፳፬

## ፖርቱጋሎቹ በኢትዮጵያ በነበሩበት ሰዓት ካዩትና ከሰሙት ውስጥ - የ፪ቱ መን ግሥታት እርስ በርስ መመራመር (፲፭፻፲፫ - ፲፭፻፲፱ ዓ. ም.)

የነሙቼብዥ ቍጥራቸው ፲፫ የሚደርሰው እነዚህ ፖርቱጊዞች እ.አው.ቍ. በ፲፭፻፳ ዓ. ም. በሚያዝያ ፲ ቀን ምጥዋ ደርሰው ከምጥዋ አልፈው ስመ ጥሩውን ገዳም ደብረ ቢዘንን ከዚያ ጥንታዊት ከተማችንን አክሱምን ጐብኝተው ከአክሱም በአ ምባ አላጌና በአሸንጌ በላስታ በኩል አድርገው በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ደብረ ሊባኖስ ደርሰው ከዚያ በጥቅምት ፲፱ ቀን ንጉሡ ልብነ ድንግል ወደሚገ ኙበት ወደ አንጾኪያ (ይፋት - ኤፍራት) እንደደረሱና የደረሰባቸውን የደጅ ጥናት ችግር አልፈው በመጨረሻ ወደ ስምምነት ከቀረቡ በኋላ ለንጉሡ መልክታቸው ንና ደብዳቤውን እንዳቀረቡ ከዚያም ያለፈውን ችግራቸውን የሚያስረሳ መስተን ግዶና ሽልማት ከንጉሡ እንደተደረገላቸው እንብበናል ።

ከመልክተኞቹ ጋር የነበረው ስሙን ደጋግመን ያነሣነው ወደፊትም የምናነ ሣው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ብልህ የቤተ ክህነት የቀለም ሰው ስለነበረ በኢትዮ ጵያ ፮ ዓመት ከነዚሁ ከፖርቱጊዞቹ ጋር አብሮ ቆይቶ ከተመለሰ በኋላ እ. አ. ቍ. በ፲፭፻፴ ዓ. ም. በፖርቱጊዞቹ ቋንቋ በኢትዮጵያ ስላየውና ስለሰማው አንድ ለዚ ያን ጊዜና ለዛሬ ዘመን ጠቃሚ የሆነ ታሪካዊ መጽሐፍ አዘጋጅቶ አወጣ ። የመጽ ሐፉ አርእስት ከዚህ በፊት እንዳልነው በፖርቱጋል ቋንቋ « VERDADERA INFORMACAM DAS TERRAS DO PRESTE JOAM ይባላል ። ትርጓሜው ስለ ቄሱ ዮሐንስ አገሮች እውነተኛው ወሬ» ማለት ነው ። ይኸው መጽሐፍ ወደ ብዙ ቋንቋ (እንግሊዝኛ ፥ ፈረንሳዊኛ ፥ ጣልያንኛ) ተተርጕሞ ሲኖር አቶ ግርማ በሻህ እ. አ. ቍ. በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ወደ አማርኛ ተርጕሞት የሊስቦን የአፍሪካ ጥናት ድርጅት አሳትሞታል ።

የአገራችንን ታሪክ ለማሙዋላት ከፍ ወገን የታሪክ ጽሑፍ ስለሚያንሰን ለግ ራኝ አህመድ ጦርነት የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ጠቃሚ እንደሆነ ይኸም የአልቫሬጽ መጽሐፍ ላዔ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ታሪክ ማሟያ የሚጠቅሙ ብዙ ጉዳ ዮች ስላሉበት እኛም እነሆ በብዙ ቦታ ጠቅሰነዋል ።

በዚሁ መጽሐፍ ላይ መልክተኞቹ በ፲፭፻፲፫ ዓ.ም. መጥተው ፮ ዓመት በኢት

ዮጵያ ሲቆዩ በብዙ አውራጃ ስለተዘዋወሩ በስድስት ዓመታት ከዩትና ከሰሙት ውስጥ አልቫሬጽ በመጽሐፉ የጠቀሳቸው ከዚህ ቀጥለው ይገኛሉ ።

ሀ. ባሕር ነጋሽ ዶሪና አሮን የሚባሉት መሳፍንት ወንድማማች አንዲት ሴት በየተራ ማግባታቸው (1) ።

ለ. ጸጋ ዘአብ የሚባለው ያዬ ልብነ ድንግል አምባሳደር ሆኖ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ከነሮድሪግ ጋር ወደ ሊስቦን ሲላክ ወደፊት እንደምናየው የካህናት አለቃ እንደነበረና የኢጣሊያ ቋንቋ በመጠኑ እንደዚሁም የፖርቱጋል ቋንቋ ማወቁ ለአምባሳደርነት እንዳስመረጠው (2) ።

ሐ. ግብጻዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ማርቆስ በ፻፰ ዓመት ዕድሜያቸው ከግብጽ ተሾመው መጥተው በኢትዮጵያ የ፶ ዓመታት ጊዜ እንዳሳለፉና በዚህ ጊዜ (፲፭፻፳፰ - ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. እ. አ. ቆ.) ዕድሜያቸው ከ፩፻፰ ዓመታት በላይ እንደ ነበረ ፤ የመጡትም አንዱ ቢሞት ሌላው እንዲተካ ተብሎ አባ ያዕቆብ ከሚባ ሉት ጋር እንደነበረና በኋላ ያዕቆብ ሞተው አባ ማርቆስ እንደተተኩ ። ጳጳስ ሚመጣ ስለማይታወቅ ገና መናገር የማይችሉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሕፃናት በናታቸው እቅፍ እንዳሉ ሌሎችም እስከ ፻፰ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ክህነ ትም ዲቁናም መቀበላቸውን (3) ።

መ. ባዬ ዘርዓ ያዕቆብ ከ[illegible] የመጣው የቬኔዚያ (ኢጣሊያ) ተወላጅ ከአባ ጊዮርጊስ ጋር በሃይማኖት የተከራከረው ባዬ በዕደ ማርያም ዘመን የኦትሮንስ ማርያ ምን ቤተ ክርስቲያን በሥዕል ያስጌጠው ብራንካ ሊዎን የሚባለው አሁንም በዚህ ጊዜ ከፖርቱጊዞቹ ጋር ተገናኝቶ ያገሩን (የኢትዮጵያን) ቋንቋ እጣርቶ በማወቁ ሉነሱ ማስተርጎሙን (4) ከርሱም ጋር ባዬ እስክንድር ጊዜ ከሠላሳ ዓመት በፊት የመጣው ፔድሮ ደ ኮቪልሐእ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ ተገኝቶ በአስተርጓሚነት መሥራቱን (5) ።

ሠ. በቤተ መንግሥቱ ያንጊዜም ወጣቶችን እርስ በርስ የማታገል ልምድ ኖሮ ከነርሱ መካከል አልአዛር ዲ አንድራዴ የሚባለው የፖርቱጋሉ ተወላጅ ገብረ ማርያም ከሚባለው የወርቅ አንጥረኛ ጋር ተጋጥሞ ባንዳፍታ ገብረ ማርያም ቅልጥሙን በትግል ጥሎ ስለሰበረው የወርቁ ዘበ ተሸልሞ አራት ሰዎች ተሸክመው ወደ ሠፈሩ ወሰደው እንዳስተኙት ። በማግስቱ ከመካከላ ችሁ ሌላ ታጋይ እንዳለ ላኩ የሚል የንጉሡ ቃል ስለመጣ ሮድሪግ የአልአዛ ርን ቁጭት ለመወጣት ብሎ እስጢፋኖስ ጋልሃርትና አይራስ ዲዝ የተባሉ ትን ሁለት ጉበዛዝት መርጦ እንደላካቸውና ወዲያው አይራስ እንደገጠመ

(1) አልቫሬጽ ምዕ. 21
(2) ,, ,, 46.116
(3) ,, ,, 98
(4) ,, ,, 85
(5) ,, ,,

አፍታ ሳይቆይ ከንዱን ቀልጥሞ ስለጣለው የተሰበረ ክንፉን አንክርፎ ወደ ድንኳኑ መመለሱን የርሱንም መሰበር ሲያይ ጓደኛው ከገብረ ማርያም እልገጥምም ብሎ መመለሱን እነዚህን ሁሉ እየታገለ የሰባበረ ያው ገብረ ማርያም የሚባለው ትክሻው ሰፊና ጡንቸኛ (በፊት እስላም የነበረ) የወርቅ አንጥረኛው መሆኑን ጽፏል ። (እዚህ ላይ የትግሉ ግጥሚያ የፈቃድ ትግል ሆኖ ሳለ ጠብና መደባደብ ያለበት ይመስል አንዱ ክንዱን ፪ኛው ቅልጥሙን ተሰበረ የተባለበት ምክንያት አይገባንም) (1) ።

ረ. ንጉሠ ነገሥቱ ከአውራጃ ወደ አውራጃ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ፶ሺ አንዳንድ ጊዜም ፻ሺ በቅሎኛ እንደሚያጅባቸው ። ከጠቅላላው አጃቢ ካሥር አንዱ ነቃ ያለና አለባበሱ ያማረ ሲሆን የቀረው ወንድና ሴት ወጣትና ደሃ ግማሽ ቸም ጨርቅና ቆዳ የለበሱ ተራ ሰዎች መሆናቸውን ፤ ከአጀቡ ጋር ፲፪ ታቦታት አብረው እንደሚጓዙ ንጉሡ አንዳንድ ጊዜ በጥቁር ዋርዳ በቅሎ ፤ አንዳንድ ጊዜ ባለአጎበር አልጋ ላይ ተቀምጠው በሰው ትክሻ እንደሚጓዙ ፣ ከንጉሡ ፊት ለፊት በሰንሰለት የታሠሩ አራት አንበሶች እንደሚሄዱ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለልደት ፣ ለፋሲካ ፣ ለመስቀል ባመት ፫ ጊዜ ሕዝቡን እየተቀበሉ እጅ ማስነሣታቸውን ፣ ይኸም የሆነበት ምክንያት ዓፄ እስክንድር የሞቱ ጊዜ ሹማምንቱ የንጉሡን መሞት ደብቀው ሦስት ዓመታት አገሩን ገዙት ስለሚባል ለመታየት መሆኑን (2) ።

ሰ. ለልደት በዓል በዋዜማው የኢትዮጵያ ካህናት ባንድ ወገን ማኅሌት ቆመው ሳለ ፖርቱጊዞችም እናንተም እንደልማዳችሁ ቀድሱ ተብለው ሌሊቱን ሲቀድሱ ንጉሡ ዜማቸው ደስ ብሏቸው በድንኳናቸው ውስጥ እንደሆኑ ከነቤተሰባቸው እያደነቁ ሲያዳምጡ ማደራቸውን (3) ።

ሸ. ንጉሡ ለጓዝ ማንሻ በሰጡአቸው አጋሠሦች ምክንያት ዋናው መሪ ዶም ሮድሪግና ዦርዥ ደ አብሬው ተጣልተው ከተደባደቡ በኋላ ስለተኳረፉና ንጉሠ ነገሥቱም ሊያስታርቁ ሞክረው በሮድሪግ እምቢተኛነት ጠባቸው እየባሰ በጉዞም በሰፈርም ሁለቱ ወገን ለይተው ለየብቻ መሆናቸውን ፤ እርቁን እምቢ በማለቱ ንጉሠ ነገሥቱ በሮድሪግ ላይ ቅርታ እንደተሰማቸው (4) ።

ቀ. በሕማማት ሰሞን ማናቸውም ሥራ መቆሙን ፤ በዚሁ ሰሙነ ሕማማት ከፍተኛ ማዕርግ ያላቸው ሰዎች ከል ነክረው ጥቋቁር ልብስ መልበሳቸውን ፤ ቄሰ ገበዙ የጸሎተ ሐሙስ ለት ልብሱን አሽርጦ በብርጩማ ላይ ተቀምጦ የብዙ ሰው እግር ማጠቡን ፤ ዓርብ የስቅለት ለት የጌታችን ሥነ ስቅለት ይገለጥና በርሱ ፊት ምዕመናኑ ለምልክት ያህል እርስ በርሳቸው በጥፊ መመታታቸ

(1) ምዕራፍ 87
(2) " 88-89
(3) " 90
(4) " 106

ውን ፤ ከዚያ ሦስቱ የቤተ ክርስቲያን በሮች በያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ቀሳውስት አለንጋ ይዘው ቆመው ከውስጥ ወደ ውጭ የሚወጣውን ሰው እንደሚጠበጥቡ ። አንዳንድ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በፈቀዳቸው ደም እስኪወጣቸው ድረስ እኩል ሰዓት ድረስ እንደሚጠበጠቡ (1) ።

በ. እ.አ.ቆ. ጥር ፲፪ ቀን ፲፰፻፸፪ ዓ.ም. (ጥር ፳ ቀን ፲፰፻፷፬ ዓ.ም.) በቤተ አምሐራ (በዛሬው ወረይሉ) አምሮ የተሠራው የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተመረቀበት ቀን ሌሊቱን ማኅሌትና ፍታት ጧቱን ቅዳሴ ተደርጎ በማግሥቱ እሑድ ንጉሡ ነገሥቱ ያባታቸውን ያፄ ናዖድን አጽም ከአሮጊው ቤተ ክርስቲያን አስወጥተው በክብር ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ሲያገቡት ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት አሮጌው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ በጣም ከማርጀታቸው የተነሣ ግራና ቀኝ ተደግፈው እየተራመዱ ሲሄዱ ከርሳቸው ፊት ለፊት ሁለቱ ንግሥታት እሌኒና ናዖድ ሞገሳ ፥ እንደዚሁም ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል ጥቋቁር ልብስ ለብሰው አጽሙ ያለበትን ሳጥን የያዘውን አጐበር እየተላቀሱ ማጀባቸውን (2) ።

ተ. ንግሥት እሌኒና ንግሥት ናዖድ ሞገሳ (፲፰፻፸፪ - ፹፬ ዓ. ም.) መሞታቸውን በንግሥት እሌኒ ሞት መኳንንቱ ሁሉ ኀዘንተኛና ቅሮተኛ እንደነበረ ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር ዋና የመልክተኞቹን ዓላማ ከመያዙ በቀር ይህ የአልቫሬዝ መጽሐፍ የዚህን ዘመን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማወቅም ለማጣራትም የሚጠቅሙ ብዙ ጉዳዮች ይዞ ይገኛልና አንባቢ እየፈለገ ሊያነበው ይገባል ። ከሌላው ተከታይ በቀር ፲፫ የፈረንጅ አባሎች ያሉበት በአምባሳደር ደረጃ የሚመራ ይኸን የመሰለ የመልክተኞች ጓድ የፈረንጅ አገር መንግሥት ከአክሱም ውድቀት ወዲህ በይፋም ያለይፋም ወደ ኢትዮጵያ ሲልክ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው ።

ሁለቱን የአፍሪካና የአውሮፓን መንግሥታት ሊያዛምድ የቻለው ከዚህ በፊት ደጋግመን የጠቀስነው በኢትዮጵያ በኩል የቱርኮቹንና የዓረቦቹን እስጊነት ለመቃወም የነርሱን አለኝተኝነት በመደገፍ አልፈው አልፈው እየሸፈቱ የሚያስቸግሩትን የአዳልን የሱማሌን ነገዶች ለመደምሰስ ሲሆን በፖርቱጋል በኩል ያለው ደግሞ በደቡብ አሜሪካ በብራዚል ፤ በሕንድ ፤ በሰሜንና በመካከል አፍሪካ ግዛታቸውን እንዳስፋፉ በዚህም መተላለፊያ በሆነው በባብኤል ማንደብ የአፍሪካ ቀንድና በመካከለኛው ምሥራቅ አዳዲስ ግዛት ለመጨመርና በማናቸውም የፖርቱጋልን መንግሥት ከፈረንሣዊና ከኤስፓኝ ከቱርክ የበለጠ ገናና ለማድረግ የጕላ ምኞት ነው ። ከዚህ የግዛት መስፋፋት ጋር አባቱ አማኑኤል ሞቶ በዙፋን የተከተለው ልጁ የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ በተደራቢ በነዚህ በሚያቀናቸው አዳዲስ አገ

(1) ምዕራፍ 111
(2) " 100
(3) " 120

ሮች ከዚህ በፊት እንዳልነው የሮማ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ሥልጣኗን እንድ ታስፋፋበትና በዙፋኑ ላይ ባለው አቅዋም በሚደግፉት እንደታላቅ አባት በሚያያ ቸው የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ዘንድ ሞገስና ሙገሳ ለማግኘት ከፍ ያለ ጥረት እንዳለው ወደፊት ንጉሡ ከሊስቦን ያዤ ልብነ ድንግልን መላክተኛ አልቫሬጽን ወደ ጳጳሱ ሲልክ አብሮ የላከው ደብዳቤ በሰፊው ያስረዳል ።

በዚያን ዘመን ባለው አስተሳሰብና መንፈስ በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካ ከል ወዳጅነቱና ዝምድናው በጥብቅ ከተመሠረተ የሁለቱ የተባበረው ኃይል የእስ ላሞቹን የሃይማኖት መደብ መካ መዲናን ለማፍረስ ፤ የጌታ መቃብር ያለበትን ኢየሩሳሌምን ከቱርክ መንግሥት ግዛት ነፃ ለማውጣት በመሪዎቹ በኩል ሰፉ ያለ ምኞት እንደነበረ በየጽሑፉ ተገልጿል ። ነገር ግን በሚቀጥሉት ፲፭ ዓመታት ግራኝ ኢትዮጵያን ከወረረና የፖርቱጋል መንግሥት ፬፻ ወታደሮች ልኮ ከግራኝ ወረራ ኢትዮጵያን ረድቶ ካዳነ በኋላ በሚቀጥለው ዘመን (፲፮ - ፲፯ኛ መቶ ዓመት) ውስጥ ፖርቱጋል እየደከመ የቱርክ መንግሥት እየጠነከረ ስለሄደ በመካከሉም ፈረንሳዊ ከቱርኩ ኤስፓኙ ከጀርመኑ የመደረብና በአውሮፓ መንግሥታት ዘንድ የመከፋፈ ልና እርስ በርስ የመዋጋት ነገር ስለመጣ ሁለቱ የአፍሪካና የአውሮፓ መንግሥ ታት የአለሙት ምኞት ፈጽሞ ሊከናወን አልቻለም ። ታላቂቱ ፖርቱጋልም በሚ ቀጥለው ጊዜ (፲፭፻፹ ዓ.ም.) በኤስፓኙ ንጉሥ በፊልጶስ ዳግማዊ ውስጥ ተጠቀለ ለች ። በኋላ ደግሞ እንደ አው.ቆ. በ፲፮፻፵ ዓ. ም. የብራጋንስ ሥርወ መንግሥት ወስዶ እስከ ፲፱፻፲ ዓ. ም. ድረስ ቀጠለ ።

የሆነ ሆኖ ፖርቱጋሎቹ ኢትዮጵያ በነበሩበት በስድስቱ ዓመታት ውስጥ (፲፭፻፳ - ፳፮ ዓ. ም. አ. አ. ቆ.) የቄሱ ዮሐንስ አገር እያሉ ከቀድሞ ዠምሮ በሩቁ ወሬውን ይሰሙት የነበረውን አገር አሁን ራሳቸው በሥፍራው ተገኝተው የዓይን ምስክር ሆነው የቤተ መንግሥቱንና የቤተ ክህነቱን ድርጅት የሥልጣኑውን የሀብ ቱን የወጉንና የሥርዓቱን የኃይሉንና የድካሙን መጠን ከሕዝቡ ኑሮና ልማድ ጋር ለማጥናትና ወሬውን ለተላኩበት መንግሥትና ለፖርቱጋል ንጉሥ እንደዚሁም ለሕንድ ጠቅላይ ገዥና ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለማድረስ ሲጣጣሩ ሰንብተዋል ። የኢት ዮጵያንም አውራጃዎች ፮ ዓመት ሙሉ ከሸዋ ወደቤተ አምሐራ (የዛሬ ወሎ) ከዚያ ወደ ኤርትራ ከኤርትራ መርከብ ሳይመጣላቸው እየቀረ ወይም የመጣው ጠብቆ አጥቷቸው ሲመለስ እንደገና ወደ ሸዋ ከሸዋ ወደ ጉራጌ ከዚያም እስከ ሐድያ (ከም ባታ ውስጥ ያለ) ድረስ ከንጉሡ ጉዞ ጋር ብቻቸውንም ከሹማምንት ጋር እየተዘዋ ወሩ በመጐብኘት በአገሩ ላይ የበቃ ጥናት አድርገዋል ። በተለይ ደራሲው አልቫ ሬጽ በኋላ መጽሐፉን ለመጻፍ የተጠቀመባቸውን አሳቦችና መሣሪያዎች ለማጠራ ቀም ጭምር ከንጉሡ ነገሥቱ ከጳጳሱ ከመኳንንቱና ከካህናቱ ጋር በየጊዜው እየተ ገናኘ አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥ ገዳማትን አብያተ ክርስቲያናትን በመጐብኘት ብዙ ወሬ አጠራቅሟል ። የተረፈውንም በኢትዮጵያ ከሐምሳ ዓመት በላይ ከተቀ መጠው ከብራንካ ሌዎንና ከሠላሳ ዓመት በላይ ከተቀመጠው ከአገሩ ተወላጅ ከደ ኮቪልሐእ እየጠየቀ ብዙ ነገር ተረድቷል ።

በበኩላቸው ንጉሡ ንጉሥቱ በርሳቸውና በፖርቱጋል ንጉሥ በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል ያለውን የኃይልና የሥልጣኔ ብልጫ የወታደር ብዛትና ትጥቅ በተዋሕዶና በካቶሊክ በሁለቱ ቤተ ክህነት መካከል ያለውን የወግና የሥርዓት ልዩነት ለማወቅ አበክረው ይጥሩ ነበር ። ለልደትና ለጥምቀት ወደ ቤተ አምሐራ ቀጥሩ በበረከተ ሠራዊት ታጅበው ሲሄዱ ንጉሣችሁ ይኸን ያህል እጀብ ይኸን የመሰለ የሐርና የወርቅ ድባብ አለውን ። በናንተ ቤተ ክርስቲያንስ ውስጥ ካህናት በማኅሌት እንደኛ ያሸበሽባሉን ካላሸበሸቡስ የኛው ሽብሸባ የሚነቀፍ ነውን ሳት ደብቅና ሳትፈራ እውነቱን ንገረኝ እያሉ በቀጥታም በመልእክትም አልቫሬዝን በጥያቄ ያዋክቡት እንደነበረ በመጽሐፉ ገልጾታል (1) ።

ነገር ግን ቀድሞም አጠገባቸው ካሉት ፈረንጆች አሁንም ከአልቫሬዝ እየጠየቁ ባጠኑት መጠን ምንም እንኳን አገራቸው ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት በጥንታዊነት በሃይማኖት አቅዋም በሕዝብና በወታደር ብዛት ከፖርቱጋል መንግሥት እንደማታንስ ቢረዱት አሁን እያደር በሚያዩትና በሚሰሙት ይህ የወዳጅነት ግንኙነት ወጥነው ለቃልኪዳን ዝምድና የተመኙት የአውሮፓ መንግሥት በእውቀትና በሥልጣኔ ከርሳቸው አገር መብለጡን በትክክል ማመናቸውን ወደፊት በምናነበው ለአማኑኤል ተከታይ ለዮሐንስ ፫ኛ በጻፉት ደብዳቢያቸው ላይ በያይነቱ አሠልጣኝና መምህራን ስለጠየቁ ይኸው ራሱ በቂ አስረጅ ነው ።

ISIC

በቅርቡም ጊዜ እርሳቸው በማኅፉዝ ጋር ሲዋጉ የሕንዱ ጠቅላይ ገዥ ሎፖ ዴአሬስ ዘይላ መጥቶ ከተማዋን ማጥፋቱ አሁንም ዲዩጎ ሎፔዝ በምጥዋ ያለውን የቱርክ ኃይል በታትኖ እነዚህን መልክተኞች ምጥዋ አራግፎ ወደርሳቸው እንዲጓዙ ማድረጉ ይህ መንግሥት ወዳጅነቱ የሚያኮራ ዝምድናውም ለወደፊቱ ለኢትዮጵያ ደኅንነት መድን እንደሚሆን በመጨረሻ ወደ መገንዘብ ደርሰው የመዠመሪያውን የፊት መንግሥትና ደጅ የማስጠናት ጊዜ አልፈው የወዳጅነት ግንኙነቱን ለማጠንከር ወስነው ይታያሉ ።

ከዚህ ሁሉ ጥናትና ግምት በኋላ በተራቸው ከነዚሁ ፖርቱጊዞች ጋር የራሳቸውን መላክተኛና ገጸ በረከት አሲዘው ለፖርቱጋል ንጉሥ እንደዚሁም ብዙ ቀን በማነጋገር በፊታቸው ሞገስና ብዙ ሽልማት ያገኘውን ፍራንቼስኮ አልቫሬዝን ወደሮማ ሊቀ ጳጳሳት መላካቸውን በሚቀጥሉት ምዕራፎች እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፳፰
## ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤል የተዘጋጀው ደብዳቤና ገጸ በረከት (፲፭፻፲፬ ዓ.ም.)

ፖርቱጊዞቹ በመጡ በሁለተኛው ዓመት እ.አ.ቆ. በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. በየካቲት ወር ዓፄ ልብነ ድንግል ከቅርብ የሥራ ጓደኞቻቸውና ሹማምንቶቻቸው ጋር ከፖርቱ

(1) ምዕ. 88 - 90. 92

ጋል አምባሳደር ይልቁንም ከብልሁና ከአዋቂው ከፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ጋር ተመ ካከረው ለንጉሡ ለአማኑኤል የሚላከውን ገጸ በረከትና ደብዳቤ ያዘጋጁ ዠመር ። ለውጭ አገር ነገሥታት ደብዳቤ መጻፍ በቂ ልምድ ስለአልነበራቸው ስለአድራሻ ውና ስለአርእስቱ ራሱ አልቫሬጽ ዋና መካሪ ሆኖ በተረፈ በደብዳቤው ላይ ስለሚ ጠቀሱት ቃሎች የሚመክሩ ብዙ ሊቃውንትና ብዙ መጻሕፍት ቀርበው እንደነበረ ደብዳቤው በኢትዮጵያ ቋንቋ (በግዕዝ መሆን አለበት) ተጽፎ ካለቀ በኋላ አንዱ መነኵሴ (ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ሳይሆን አይቀርም) እያነበበው መነኵሴው የሚያነበውን ባዔ እስክንድር ዘመን መጥቶ በኢትዮጵያ የሚኖረው ፔድሮ ደ ኮቪ ልሐእ የሚባለው ወደ ፖርቱጋል ሲተረጉመው የመልክተኞቹ ጸሐፊ ዮሐንስ ኤሽ ኮላር (JOAO-ESCOLAR) የሚባለው ደግሞ በደብዳቤ መልክ በጽሑፍ ሲያሠፍ ረው ራሱ አልቫሬጽም አብሮ ሆኖ ይረዳ እንደነበረ ለንጉሥ አማኑኤልና ለሕንድ ጠቅላይ ገዥ በኢትዮጵያና በዓረብኛ በፖርቱጋልኛ በሦስት ቋንቋ ከሦስት ላይ ቃሉ ተጽፎ ከየቋንቋው አንዳንድ ቅጅ ተወስዶ በወርቀ ዘቦ ከረጢት ውስጥ አድ ርገው እንዳስረከቡዋቸው ራሱ አልቫሬጽ በመጽሐፉ ይገልጻል (1) ።

ከዚህ እያይዞ ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉንም መላክተኞቹ ከፊታቸው አስጠርተው የወርቅ ዘቦና የሐር ልብስ ሸልመው ለሮድሪግ ፴ ወቄት ወርቅ ለጭፍሮቹ (፲፫ ሰዎች) የሚካፈሉት ሃምሳ ወቄት ወርቅ እንደሰጡአቸው ከዚያ በወርቅና በብር የተሠራ አንድ ትልቅ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ የጨርቅ ጉዝጓዝ ባለበት አገልግል ውስጥ ተሰጉሞ ዘውዱን በንጉሠ ነገሥቱ ስም አብዲናጎ የሚባለው የልፍኝ አሽከ ሮች አለቃ ለሮድሪግ ሲያስረክብ "ዘውድ ካባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የከበረ ነገር ስለሆነ እኔም እርስዎን እንዳባት ስለማይዎ ይኸን የከበረ ዘውዴን ከራሴ ላይ አን ስቼ ልኬልዎታለሁ" ብለዋል ፤ ብሎ ነግሮ ለንጉሡ ለአማኑኤል እንዲያስረክብ ይነ ግረው ዘንድ ከንጉሠ ነገሥቱ መታዘዙን ይገልጻል (2) ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤልና እርሱ ከሞተ በኋላ ለልጁ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉዋቸውን ዋናዎቹን የግዕዝኛ ደብዳቤዎች ወይም የግል ባጫቸውን ፎቶ ማግኘቱ በታሪካዊ ሰነድ ረገድ ከፍ ያለ ዕድል ነበር ። ነገር ግን ከአ ራት መቶ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው እነዚህ ደብዳቤዎች በሊስቦን ቤተ መጻሕ ፍት ስለማይገኙና እስካሁን የፖርቱጋልም የሌላም አገር ደራሲ የግልባጩን ፎቶ አሳትሞት አያውቅም ። አልቤር ካሜረር የሚባለው ደራሲ ደብዳቤዎቹ ከሊስቦን ቤተ መንግሥት በፍጹም መጥፋታቸውን ያረጋግጣል (3) ።

ነገር ግን አልቫሬጽ እ. አ. ቆ. በ፲፭፻፳፮ ዓ.ም. ወደ አገሩ ከተመለሰ ወዲህ በ፲፭፻፵ ዓ. ም. በጻፈው መጻሕፍት ውስጥ የደብዳቤዎቹን ቃላት በፖርቱጋል ቋንቋ ጨምሮ አሳትሟቸው ይገኛል ። ከዚያ ላይ ይኸን መጽሐፍ ወደ የቋንቋቸው

(1) የአልቫሬጽ መጽሐፍ በነአቶ ግርማ በሻህ ትርጉም ምዕራፍ 105

(2) " " ምዕ 106

(3) La Mer Rouge Portugais et Abissins devant Islam 1er partie ገጽ 52 ። ነገር ግን በቅርብ ጊዜ ከዚያ ተገኘ የተባለውን የግዕዙን ደብዳቤ ለዮሐንስ ፫ኛ የተጻፈውን ወደፊት እናንባለን ።

እየተረጐሙ ያሳተሙ ሁሉ አውጥተውት ይገኛል ።

ከነዚሁ መካከል ሎርድ ስታንሌይ እና አልዱርለይ ናራቲቭ እና ዘ ፖርቱጊዝ ኤምባሲ በሚል አርእስት በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. በእንግሊዝኛ ፤ ዣን ቱምፖራል የሚባለው አፍሪካ በሚል አርእስት በፈረንሳዊኛ ከሌሎች የአፍሪካ ታሪኮች ጋር አትመውት ይገኛል ። በዚሁ በጎርን ቱምፖራል መጽሐፍ ላይ ይህ ደብዳቤ በየጊዜው ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጐሙን ፤ የመጀመሪያው ዋናው ያፄ ልብነ ድንግል ደብዳቤ በሐበሻ ቋንቋ የተጻፈ መሆኑን ሲያመለክት በግዕዝ ወይም በአማርኛ መጻፉን አይለይም ። ይሁን እንጂ በግዕዝ ለመሆኑ አያጠራጥርም ። ስለዚህ ይህ ደብዳቤ ከግዕዝ ወደ ፖርቱጋል ተተርጉሞ ንጉሡ ዮሐንስ ከተመለከተው በኋላ ቀጥሎ በጉዳዩ የሚገባው የሮማ ሊቀ ጳጳስ ይመለከተው ዘንድ ወደ ላቲንና ወደ ቶስካን ተተርጉሞ ከቶስካን (የቀድሞ መደበኛ የኢጣሊያ ቋንቋ) ወደ ቀድሞው ፈረንሳዊኛ መተርጐሙን ያመለክታል ።

በመጨረሻ ደግሞ ከመጀመሪያው እትማት ላይ ሳይሆን ከ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. (እ. አው. ቀ.) እትማት ላይ በፖርቱጋል ቋንቋ ከተተመው ላይ ለው የፖርቱጋል ታሪካዊ ጥናት ክፍል (CENTRO DE ESTUDOS HISTORICOS ULTRAMARINOS) የሚባ ርኛ አስተርጉሞ "ኢትዮጵያ ፖርቱጊዞች እንዳዩዋት" በሚል ስያሜ አሳትሞ አው ጥቶታል ።

ISIC

ስለዚህ ይህ ከፖርቱጋሉ አቶ ግርማ በሻህ የተረጐሙት የበለጠ ትክክለኛ ይሆናል በማለት ከዚሁ መጽሐፍ ላይ በቀጥታ ተገልብጧል ። ይሁን እንጂ ከዣን ቱምፖራል ከቀድሞው ፈረንሳዊኛ ጋር በማስተያየት አንዳንድ ለራሴ የመሰለኝን በደብዳቤው ግርጌ በምልክት ለማብራራት ሞክሬያለሁ ።

ስለዚህ የኢትዮጵያና የፖርቱጋል ሊቃውንት በደብ ያዘጋጁትን የዚህን ደብዳቤ ቃሉን ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«ሁልጊዜም በነበረውና መጀመርያም በሌለው በአብ ስም ፤ ባንዱ እንዳባቱ በማይታየው የውቅያኖሶቹ መሠረት ከመጣሉ በፊት የከዋክብት ብርሃን በነበረው ያለ ወንድ ዘር ወይም ያለጋብቻ በድንግል ማኅፀን በተጸነሰው በወልድ ስም ፤ ማናቸውንም ምሥጢር በሚያውቀው ያለምሰሶ ከቆመው ከሰማይ በመጣው ምድርንም በዘረጋው በጰራቅሊጦስ ስም ፤ እርሱ አንደኛ ወይም ሁለተኛ ሳይሆን ማናቸውንም ነገር ከፈጠረው አምላክ የተገኘ ሥላሴ ነው ፤ ለሁሉም አንድ መካርና አንድ ቃል ነው ። ለዓለም ወለዓለመ ዓለም አሜን (1) ።

ይህ ደብዳቤና ኤምባሲ የተላከው ከልብነ ድንግል ነው ፤ ይህ ስም የጥምቀት

(1) የጸፉት በግዕዝ ቋንቋ ስለሆነ እንደዘመኑ የአጻጻፍ ልማድ የደብዳቤው መጀመሪያ "በስመ እግዚአብሔር አብ ዘእልበ ቅድምና . . ወበስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ዋሕድ ዘዕሩይ ምስለ አብ ." የሚል መሆን አለበት ። ይህም አብዛኛው እንጋገር ፫፻፲፰ ሊቃውንት በኒቅያ ጉባዔ ከወሰኑት የእምነት መሠረት ከሆነው ከጸሎተ ሃይማኖት ላይ የተወሰደ ቃል ነው ።

ስሙ ሲሆን ከነገሠ በኋላ ዓፄ ዳዊት የተባለ የግዛቶቹ መሪ (1) ። እግዚአብሔር ያፈቀረው ፤ የሃይማኖቱ ምሰሶ ፤ የይሁዳ ነገድ ዘር (2) ። የዳዊት ልጅ ፤ የሰሎሞን ልጅ፤ የዓምደ ጽዮን ልጅ ፤ የዘርዓ ያዕቆብ ልጅ ፤ የበዕደ ማርያም ልጅ ፤ የናዖድ የሥጋ ልጅ ። የደጋው ኢትዮጵያና የሌሎችም ታላላቅ ግዛቶች ንጉሠ ነገሥት (3) ። የሸዋ ፤ የጋፋት ፤ የፈጠጋር ፤ የአንጎት ፤ የቦራ ፤ የባሌና የገንዝ ፤ የሐዲያ ፤ የቡግናና የጐጃም ፤ የአማራና የበጌምድር ፤ የዶንቢያና የዋግ እንዲሁም ንግሥት ሳባ የነበረችበት የትግሬ አውራጃ ፤ ግብጽን የሚያዋስነው የባሕር ነጋሽ ግዛት ንጉሥ (4) ።

ይህ ደብዳቤ የተላከው ለንጉሥ አማኑኤል ነው ። ሁል ጊዜ ድል የሚነሣው ፤ በእግዚአብሔር ፍቅር በሚኖረው በካቶሊክ ሃይማኖት በጸናው የጴጥሮስና የጳውሎስ ልጅ ፤ የፖርቱጋልና የአልጋርቭ ንጉሥ ፤ የክርስቲያኖቹ ወዳጅ ፤ የእስላሞችና የአሕዛብ ጠላት ፤ የአፍሪካና የጊኔ ፤ የማዳጋስካር ፤ የቀይ ባሕር ፤ የዓረቢያ የፋርስ (5) የሆርሙዝ ፤ የሕንድና በውስጡም የሚገኙ ከተማዎች ጌታ ፤ የእስላሞችና የአሕዛብ ድል አድራጊና ዳኛ ፤ የብዙ ምድሮች ጌታ ። ያለጦርና ጋሻ በየሱስ ክርስቶስ በመረዳትና በሃይማኖቱም በማመን ብቻ እስላሞችን . . . . . . ላባረሩዋቸው ለንጉሥ ዶም አማኑኤል ሰላም ለርስዎ ይሁን ። የየሱስ ክርስቶስና የመድኃኔ ዓለም እናት አገልጋይ ለሆነችው ለባለቤትዎ ሰላም ይሁን ። ለአበባዎቹ ለወንዶቹ ልጆችዎ ሰላም ይሁን ። እንደ ቤተ መንግሥት ላጌጡት [illegible]ቶቹ ልጆችዎም ሰላም ይሁን ፤ የቅዱሳን ዘር ለሆኑት ለቤተሰቦችዎም ሰላም ይሁን ። በመጽሐፍ እንደተጻፈው የቅዱሳን ልጆች የተባረኩና በቤታቸውም በጸጋ ታላቅ ናቸው ። ላማካሪዎችዎ ፤ ላገልጋይዎችዎ ለመኳንንቶችዎና ለዳኞችዎ ሰላም ይሁን ። ለታላላቅ ከተማ

(1) በዣን ቴምፖራል የደብዳቤ ትርጉም ላይ "ስሜ ሰጣን (ልብነ) ድንግል" ካለው ቀጥሎ "ትርጉሙ ድንግል ያበራችለት" ብሎ ይተገባል ።

(2) ዳዊት ፍቁረ እግዚእ ዘእምነገደ ይሁዳ ሲል "እግዚአብሔር የወደደው" የሚለው የሸኢልን ንጉሥ እንጂ የኢትዮጵያውያን ንጉሥ ዳዊት የተባሉትን ልብነ ድንግልን አይደለም ። ስታንሊ ደና ዣን ቴምፖራል የናሁ ልጅ በማለት አሳስተዋል ። ናሁ ያሉት ናዖድ ለማለት ነው ።

(3) ነገሥታቱ ባጸጸፋቸው ብዙ ጊዜ የደጋውና የቆላው ኢትዮጵያ አንዳንድ ጊዜ የላይኛውና የታችኛው ኢትዮጵያ ይላሉ ።

(4) ብዙዎች የግዛት አገሮች ዛሬም ስማቸውን እንደያዙ ወደ ጊዜያችን ስለደረሱ አንባቢ አይቸገርም። አንዳንዶቹ ቀድሞ ትልቅ አውራጃ ሆነው በኋላ እየመነመኑ ቀበሌዎች ይሆናሉ ። ጋፋት አባይ ፍርዳዋት ጐን አንጐት በላስታና በዋድላ በእንደርታና በዋጅራት መካከል የነበረ በዚህ ዘመን ትልቅ አውራጃ ፤ ቦራ ያፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ሥዩመ ሠራዊ ፪ ሐማሴን ከንቲባ ይልና ሥዩመ ቡር ይለዋል የቀድሞ የኢትዮጵያን ካርታ የሠሩ ተምቢን አጠገብ "ቦራ" ብለውት ይሆናል ፤ ገንዝ ዛሬ ግንጭ (አምቦ) የተባለው መሆን አለበት አካባቢው ሁሉ ተጠቃሎ ገንዝ ይባል ነበር ፤ የበዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ያነሣዋል ገጽ 112 ፤ 148 ። ሐድያ (ከምባታ ውስጥ) ቡግና በላሊበላ ስሜን በዘመናቸው ታላላቅ ነበሩ ። ይኸኛው አድአን ሲዘል የቴምፖራልና የእንግሊዙ ይጨምራል ።

(5) የዓረቢያና የፋርስ . . . . . . ጌታ ያሉት በማጋነን የተጨመረ እንጂ የፖርቱጋል መንግሥት እነዚህን አገሮች አልገዛም ።

ዎችና በውስጣቸውም ለሚኖሩ ለክርስቲያኖች ብቻ (አይሁዶችና እስላሞች ሳይ ጨመሩ) ሰላም ይሁን ። በክርስቶስ ላሉት ለገዳሞችና ለታላላቅ ሰዎች ሁሉ ሰላም ይሁን ።

አባቴ ንጉሥ ሆይ (1)፤ የማቴዎስን መምጣት በሰሙ ጊዜ ሊቀ ጳጳሳትን ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች እስጠሩ ማለትን ሰማሁ። ስለዚህ በጣም በመደሰቴ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን ሕዝቡም ከኔው ጋር ተደስቶአል ። ስለማቴዎስ በጠየቅሁ ጊዜ ከርስዎ አገር እንደተመለሰ በኢትዮጵያ ምድር ሲደርስ በደብረ ቢዘን ገዳም ሞቶ ሲሉ ነገሩኝ ። ይህን ሰው በአምባሳደርነት የላከሁት እኔ ሳልሆን በሞግዚትነት አገሩን ትመራ የነበረችው እቴጌ እሌኒ ነበረች ። አባቴ ሞቶ ዘውዱን እንደጫንሁ ያሥራ አንድ ዓመት ወጣት ስለነበርሁ ስለኔ ሆና አገሩን የምታስተዳድርልኝ እርስዋ ነበረች ። ማቴዎስ ከዚያ በፊት ነጋዴ የነበረ አብርሃም በሚያሰኝ መጠርያ የሚታወቅ ነበር፤ ነጋዴ መስሎ ሸቀጥ አስይዞ የእስላሞችን አገር አቋርጦ በማለፍ ደቡል ሩት (2) ። ማቴዎስም በንደዚህ ያለ አይጋ ላይ መውደቁን በተረዳ ጊዜ የኔ አምባሳደር መሆኑንና ወደርስዎም የላክሁት መሆኑን በመግለጽ የሕንድ ጠቅላይ ገዥዎ ከግዞት እንዲያወጣው በመለመን ላከበት ። ጠቅላይ ገዥውም ይህን እንደሰማና ይልቁንም ክርስቲያን መሆኑን ሀብቱ ሁሉ ተወርሶ በእስር ቤት መግባቱን በሰማ ጊዜ ሰዎችና መርከቦች ልኮ እስላሞቹ እንዲገደሉና ማቴዎስም በቶሎ ከግዞት ወጥቶ የታሠረበት ምክንያት እንዲጣራ አዘዘ ።

ጠቅላይ እንደራሴውም ማቴዎስን "ከኢትዮጵያ ንጉሥ ንግሥት ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ የምትወስደው መልእክት ምንድነው " ብሎ ሲጠይቀው መልእክቱን በገለጸ ጊዜ እንዲሄድ ፈቀደለት (3) ። ከዚህም በኋላ እርስዎ ፊት ቀርቦ እነሆ የክርስቶስ መስቀል ሲል መስቀሉን አበረከተዎ ። ብዙም ነገሮች የነገረዎ ከመሆኑ በላይ የጠየቁትን ጥያቄዎች መለሰልዎ ። ስለዚህ ግርማዊነትዎ (በደብዳቤዎ እንደተረዳሁት) ማቴዎስን አክብረው ታላቅ ሰው አደረጉት ። እርሱም ወደዚህ አገር ከተመለሰ በኋላ በደብረ ቢዘን ገዳም ሞተ ። ከርሱ ጋር የመጡ ፖርቱጊዞች እርስዎ የላኩትን ደብዳቤ አቀረቡልኝ ። ደብዳቤውን ባቀረቡልኝ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገ

(1) ዣን ቴምፖራል "Monseigneur et Père" ጌታዬና አባቴ ሆይ ይላል ፤ የሎርድ ስታንሌይ የእንግሊዝኛው ትርጉም (My Phather King) ይላል ገጽ 390

(2) ክርስቲያኑ ማቴዎስ የመልእክቱን ጉዳይ ለማከናወንና ከቱርኮችና ከዓረቦች ቁጥጥር ለማምለጥ ሲል ክርስቲያናዊ ስሙን ማቴዎስን የቀድሞ አጠራሩን አብርሃምን ለውጦ በእስላማዊ ስያሜና አጠራር ኢብራሂም (አብርሃም) እየተባለ ምናልባትም ራሱን እንደ ዓረብ አሥር ግልድም አገልድሞ ይጓዝ ነበር ማለት ነው ።

(3) ጠቅላይ የሕንድ አገረ ገዥ በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው አልፎንሶ ዶ አልቡኬርክ ነው፤ እርሱም በእንደራሴነት ሕንድን የገዛበት ጊዜ እንደ አው ቁ 1509 - 1515 ዓ ም ነው ።

ነሁ ። በርስዎና በሕዝብዎም ተደስቻለሁ ። ወደዚህ አገር የመጡት ፖርቱጊዞች በራሳቸው ፤ በእጃቸውና በደረታቸው ላይ ያደረጉትን መስቀል በማየት በጣም ተደስትሁ ።

የናንተን እምነት ጠይቄ ክርስቲያን መሆናችሁን በነገሩኝ ጊዜ እንዲሁም ከዚህ በፊት ወደዚህ ያልመጡ ሰዎች ለመገምገርያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጣን ባሉኝ ጊዜ በጣም ተሸበርሁ (1) ። ወደ ኢትዮጵያ የሚወስደውን መንገድ ፈልገው ባለማግኘታቸው ተስፋ ቆርጠው ይልቁንም ነጎድጓድንና ከንቱ ልፋትን በመፍራት ወደ ሕንድ ለመመለስ ከቆረጡ በኋላ ሌሊት በኢትዮጵያ ምድር አግጣጫ በሰማዩ ላይ ቀይ መስቀል አዩ ። ይህን መስቀል በመርከቡ የነበሩት መኳንንትና መርከበኞቹም ሰገዱለት ። ይህን ምልክት ባዩ ጊዜ መንገዳቸውን የሚመራቸው እግዚአብሔር መሆኑን ተረዱ ። እኔም በዚሁ በጣም ተደነቅሁ ። በእውነተኛው ይህ ምልክትና ቃል የመጣው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰይጣን አይደለም ። የመጣበትም ምክንያት እርስዎ ኤምባሲ እንዲልኩልኝ ለማሳሰብ ነው ። "አንድ የፈረንጅ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገኛሉ ፣ ሰላምታም ይሰጣጣሉ ፡" የሚል በቅዱስ ፊቅጦር ትንቢት ላይ በቅድሳት አበዋትም መጽሐፍ ውስጥ በነቢዩ ተሰጥቶአል (ተነግሯል) ። ይህ ትንቢት በኔ ጊዜ ይፈጸማል ብዬ ከቶ አልገመትሁም ነበር (2) ። ማናቸውንም ነገር እግዚአብሔር አውቆታልና ለስሙ ምስጋና ይድረሰው ። እኔም ለርስዎ ለአባቴና ለወዳጄ መልእክት እንድልክብዎ[illegible]ለት እግዚአብሔር ራሱ የርስዎን ኤምባሲ አዘዘልኝ ።

ከዚህ በፊት ከክርስቲያን ንጉሥ መልእክተኛ አልደረሰኝም ነበር ፤ አሁን ግን እርስዎ ቀረቡኝ ። ከዚህ በፊት ወደኔ የመጡት እነዚያ . . . . የመሐመድ ልጆች እስላሞች ብቻ ነበሩ ። ሌሎቹም እግዚአብሔርን የማያውቁ ባሮች ነበሩ ። ሌሎቹም ለእንጨት ፣ ለእሳት ፣ ለፀሐይና ለእባብም የሚሰግዱ ነበሩ ። በእውነት ስለማያምኑ እውነቱን እንዲያገኙ በማለት በማስተማር ብዙ ለፍቼ ነበር ። አሁን ግን በኔ ዘመነ መንግሥት የእረፍትና የሰላም ጊዜ ሆኖአል ። በአገሬ ድንበር ሁሉ የሚያጋጥሙኝ እስላሞች ከቶ ቀና ብለው ሊያዩኝ አይደፍሩም ፤ ወይም ፊታቸውን ከቶ ወደኔ አይመልሱም ። የጦር ሹማምንቶቼ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ድል ይነሣሉ ። እኔም

(1) "I felt Vexation" ለሚል ትርጉሙ "ብስጭት ተሰማኝ" ማለት የሚሻል ይመስላል ። የሱርድ ስታንሊይ ትርጉም ገጽ 392 ።

(2) ከዚህ በፊት በንግሥት እሌኒ ደብዳቤ ላይ እንዳመለከትነው በገድለ ፊቅጦር መጽሐፍ ፬ . . . . በኢትዮጵያ ክርስቶስ የወደደው ቅዱስ ሰው ይነግሥና ወደ ግብፅ ሄዶ እስላሞችን (ተንባላት) ያጠፋል . : . . . . . ወልደ እንበሳ ከተባለ ከቍስጥንጥንያ ንጉሥ በግብፅ ይገናኙና ከሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር በኅብረት . . . . . . የክርስትናን ሃይማኖት ያጸናሉ" ይልና እልፍ ብሎ በሌላ ገጽ "ግብፅ ኢትዮጵያ ሮም ሶስቱ ስምምነት አድርገው የኢትዮጵያና የሮም ንጉሥ ሁለቱ በሰላምና በስምምነት ሲለያዩ በዓለም ሁሉ ደስታ ይሆናል . . . . ." ብሎ ሰማዕቱ ፊቅጦር ለእናቱ ለማርታ በሕልሟ ታይቶ እንደነገራት ያረጋግጣል ። ገድለ ፊቅጦር (Corpusco) ያሳተመው ገጽ 243 - 244 ።

እንዲሁ ድል እንሣለሁ ። እግዚአብሔር ቸርነቱን አልነሣኝም ። በዳዊት መዝሙር እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎአል ። "እግዚአብሔር በኃይልህ ተደሰተአል ፣ በደህንነትህ ንጉሡና ሌሎቹም ይደሰታሉ ። ለያንዳንዳቸውም የጠየቁትን ይሰጣል ፣ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን" (1) ። ለርስዎ ላባቱ እግዚአብሔር ዓለምን ሰጠዎ ። የአሕዛብንም አገር ለዘለዓለም ሰጠዎ ። እስከ ኢትዮጵያ ግዛት ድንበር ያሉት የሌሎች አሕዛብ አገሮች የርስዎ ግዛት ናቸው ። እግዚአብሔር ብዙ ዓለሞች ሰጥቶኛል ፤ ለዚሁም አመሰግነዋለሁ ።

ልጆችዎ እውነቱን እንዲያውቁ በማለት ለርስዎ ታላቅ ቃል እናገራለሁ ፣ እግዚአብሔር ለኔና ለርስዎ ማናቸውንም ነገር ስለሰጠን መደሰት አለብን ። በክርስቶስ ላይ ባመጹት በነዚያ . . . . . እስላሞች እጅ የምትገኘውን ኢየሩሳሌምን እግዚአብሔር በእጅዎ እስኪያገባልዎ ድረስ ጸሎትዎን አያቋርጡ ። ይህ ከተከናወነ በኋላ ከርስዎ የበለጠ ኃይል ሊኖር አይችልም ። ይህን ጉዳይ በጣም ሳስብበትና ስጠብቀው ነበር ፤ ሁላችንም የጌታችን የየሱስ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን ። ይህን ባከናወኑ ጊዜ የብዙ ሰዎች ምስጋና ይደርስዎታል ።

አብርሃም የሚያሰኝ የቀድሞ ስሙን ለውጦ ማቴዎስ ይባል ከነበረው ሰው ጋር በላኩዋቸው መልእክተኞችዎ አማካይነት የርስዎ መልእክት ደረሰኝ ። ከነዚህ መልእክተኞች ሦስቱ በመንገድ ሞቱ ፣ የሕንድ ግዛትዎ እንደራሴ ከመልእክተኞቹ ጋር እምጽዋ ድረስ ሔዶ ከባሕር ነጋሹ ጋር ከተገናኘ በኋላ መልእክተኞቹን ወደዚህ ላካቸው ። የርስዎን ዝና ከነዚህ ሰዎች በሰማሁ ጊዜ በጣም ተደሰትሁ። የርስዎ ስም ከዓለም ከሚገኘው ሀብት ወይም ከማናቸውም የከበረ ድንጋይ የበለጠ ነው ። የርስዎን ዝና የሰማሁት በታላቅ ደስታ ነው ።

እኔም ሁለት መቶ ሺህ ወርቅ እሰጣለሁ (2) ። ከዚህ በኋላ በወዳጅነት እንገናኛለን ። የኔን ምኞት ለመፈጸም እርስዎ መልእክተኞች ቢልኩ እኔስ የሰላም መልእክተኛ ለምንድን ነው ያለመላኬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም እርስዎ አስቀድመው መልእክተኞች ወደኔ ላኩ ። የክርስቶስ አንድ ልብና አንድ ፈቃድ እንደነበራቸው ሁሉ የርስዎ መልእክት በደረሰኝ ጊዜ በጣም ተደሰትሁ ። ዕድሜ የማያውቀው ለዘለዓለም የሚኖረው አንዱ እግዚአብሔር እርስዎን አባቴን ንጉሥ አማኑኤልን ይጠብቅዎ ።

(1) እግዚእ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ ወብዙኃ ይትሐሠይ በአድኅኖትከ . . . . . መዝሙር 20 ።
(2) Jean Temporal "En vous promettant dès maintenant de vous fournir ከተረጐመው ላይ « mile fois cent mile drachmes d'or". » ሺ ጊዜ መቶ ሺ ስለሚል መቶ ሚሊዮን የወርቅ ድራህም ይላል ማለት ነው ። ሎርድ ስታንሌይ በተደረጐመው የእንግሊዝኛው ላይ " I would give two hundred millions of gold " ሁለት መቶ ሚሊዮን ይላል ገጽ 394 ። ስለዚህ የደብዳቤዎቹ ትርጉሞች ይኸን በመሰለ አኳኋን በሌሎችም ዓረፍተ ነገሮች ላይ ይለያያሉ ። ድራህም ጥንት ግሪኮች የሚገበያዩበት የወርቅ ገንዘብ ነው ። ነገር ግን ባቄ ልብን ድንግል ዘመን ድራህም የሚባል የብርም የወርቅም መገበያያ ገንዘብ ስለሌለ እዚህ ላይ ግን ቱም ምራል ድራህም ያለው ቁርጥራጩን የወቄት ወርቅ ይሆናል ።

በግርማዊነትዎ ትእዛዝ እንደራሴዎ የላካቸው መልእክተኞች ሁሉም መልካም ሰዎች ናቸው ። በዶም ሮድሪግ ዶ ሊማ አምባሳደርነት የመጡትን መልእክተኞች ሁሉ በክብር ተቀበልኋቸው ። አምባሳደሩን በተለይ አስደሰትሁት ። አባ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን ባነጋገሩና እንዲሁም ሃይማኖት ነክ በሆነ ጉዳይ ሁሉ እውነተኛ ሰው ሆኖ ስላገኘሁት ልዩ ክብርና ፍቅር አሳይቼዋለሁ ። የግዛታችን ጠረፍ የሆኑትን ምጽዋን ዳህላቅንና ዘይላን እንዲገዛና ወደ የግዛታችን ጠረፍ ወደ ክርስትናም እንዲመልሳቸው ይሾሙት ዘንድ እለምንዎታለሁ ። እነዚህን ስማቸው የተጠቀሱትን ቦታዎች ለርሱ ሰጥተነዋል ።

ሥልጣን የሰጠነው መሆኑን ለማረጋገጥ መስቀልና ዘንግ በእጁ ሰጥተነዋል ። ስለዚህ የተባሉት ቦታዎች ኤጲስ ቆጶስ ይሆን ዘንድ ይፍቀዱለት ። ይህን ማዕርግ ለማግኘት የበቃ ችሎታ ያለው ሰው በመሆኑ ነው ።

እርስዎም ጠላቶችዎን ከእግርዎ ሥር ለመጣል እንዲችሉ እግዚአብሔር በጎ ነገር ያድርግልዎ ፤ ያበርታዎም ። እግዚአብሔር ዕድሜዎን ያርዝመው ፤ እኔ ራሴ የምመኘውን የመሰለ በሰማያዊ መንግሥት ሥፍራ ያዘጋጅልዎታል ። በዓይኔ ያላየኋቸውን መልካም ነገሮች በጆሮዬ ሰማሁ ። አሁን ግን ዓይኖቼ ያላሰቡትን መልካም ነገሮች አዩ ። እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሁሉ በጎ ነገር እንደሚያደርግላቸው ሁሉ ለርስዎም እንዲሁ ያድርግልዎ ። የርስዎ ቦታ በሕይ[illegible]መርከብ ላይ ይሁን መኖሪያዎም በቅዱሳን መኖሪያ ትሆን ዘንድ አሜን ።

የኔ አምባሳደር ሆኖ የምፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲነግርዎ ሊቀ ካህናቱን ልኬ የለሁ ። እንዲሁም የግል ጉዳዬ የሆነውን ለሮም ያለኝን ታዛዥነት እንዲገልጽልኝ አባ ፍራንቼስኮን ወደ ሮም ጳጳስ ልኬዋለሁ ። ትንሽ ልጅ የሚያደርገውን ሁሉ በመዘርዘር ለአባቱ እንደሚገልጸው ሁሉ እኔም አምባሳደሮች ሲልኩብኝ ማናቸውም ነገር እንዲሁ እገልጻለሁ ። እርስ በርሳችን እንድንረዳዳ ሁል ጊዜ ይጻፉልኝ ። እርስዎ የሚልኳቸውን ሰዎች በምጽዋና በዳህላቅ ደሴቶች በደረሱ ጊዜ እርስዎ የሚያዙትን ነገር ሁሉ ላደርግላቸው ዝግጁ ነኝ ። ይህንንም የማደርገው እንድንረዳዳ ስለምፈልግ ነው ። ከላይ የተጠቀሱት ቦታዎች የኔ አገር ክፍሎች ስለሆኑ ዜጎችዎ በዚያ እንደደረሱ እኔም በዚያው እገኛለሁ ። በዚያ የሚኖሩት አሕዛብና እስላሞች ብቻ ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች አይገኙም ። ዜጎችዎ በኔ ግዛት ድንበር ላይ ስለሚሰፍሩ በጣም ተደስቻለሁ ። ስለዚህ እርስዎ የለመኑትን የምፈጽም እንድንረዳዳ ነው ።

በወርቅና በብር ፤ በመዳብና በብረት በአረርም ምስሎችን ለመሥራት የሚችሉ የጅ ጥበበኞች ይላኩልኝ ። በኛ ፊደል መጻሕፍት ለማተም ይቻል ዘንድ የኛን ፊደል ለመቅረጽ የሚችሉ ጥበበኞች ፤ እንዲሁም ለጌጥ የሚሆን የወርቅ ቅጠል ለመሥራት የሚችሉ ሠራተኞችም ይላኩልኝ ። እነዚህ ሠራተኞች ሁሉ የኔ በጎ አስተያየት ሳይለያቸው ከኔ ዘንድ ይኖራሉ ። በገዛ ራሳቸው ፈቃድ ወደ አገራቸው ለመሄድ የተነሡ እንደሆነ ላስቀራቸው የማልሞክር መሆኔን በሕያው እግዚአብሔር ልጅ በየሱስ ክርስቶስ ስም አረጋግጣለሁ ። ይህን መልእክት መላኬ የርስዎን

ደግ ሰውነትና መልካም ባሕርይ ስለማውቅ ነው ። ይብ ሁሉ የተደረገልኝ ውለታ ለአብርሃም እንደተደረገለት ይቆጠራል (1) ። ስለዚህ ይህን ልመና ማቅረቤ በዚህ በመተማመን ነው ፡ ለሚፈጸሙልኝ አገልግሎት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነኝና ልመናዬን እንደ ነውር እንዳይቆጥሩብኝ እለምንዎታለሁ ። እርስዎ አባቴ ነዎ ፤ እኔም ልጅዎ ነኝ ። ስለዚህ ልጅ የጠየቀውን አባት እምቢ አይልም ። እርስዎና እኔ እንደ ግድግዳ ግንብ ድንጋዮች የተያያዝን ነን ። እንዲሁም የዓለም ጠቅላይ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተሳሰርን ነን ። እንዲሁም ከርሱ ጋር ያሉ ሁሉ እንደ ግንብ ግድግዳ ድንጋይ ባንድነት የተያያዙ ናቸው ።»

ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል በዚህ ረዥም ደብዳቤያቸው ላይ እንግዶቹን ሳይቀበሉ ወር ሙሉ ደጅ ያስጠኑበትን ምክንያት ምልክቱን አላሳዩም ። ንጉሡ ከፖርቱጋል ንጉሥ ከአማኑኤል ጋር እንደ አባትና እንደ ልጅ በቃል ኪዳንና በፍቅር ለመተሳሰር አለኝ የሚሉት ያሁኑ የጋለ ፍቅርን የያዘው ደብዳቤና የዚህኑ አገር ንጉሥ መልክተኞች በመዠመሪያው ወር ላይ ሳይቀበሉ ረዥም ቀናት በቸልታ ደጅ ያስጠኑበት ሁለቱ ሁኔታ ሊገናዘብ አይችልም ። መቼም ሰው ሁሉ የሚጸፈውና የሚያደርገው ሁል ጊዜ ሲለያይ መታየቱ ባዔ ልብነ ድንግል አልተዠመረም ።

ቀጥሎ በእስላሞቹ እጅ የሚገኘውን ቅዱስ መቃብር ያለበትን ኢየሩሳሌምን ማስለቀቅ አለብህ ብለው ለአማኑኤል ሲመክሩ በአሁኑ ጊዜ በሶሊያማን የሚመራውን የቱርክን ገናንነትና ኃያልነት ከርሱ ከሚያንሰው ከፖርቱጋል ኃይል ጋር እንዳላመዛዘኑት ያሳያል ። በምጥዋና ባንዳንድ በተበታተኑ የወደብ ከተማ ላይ እንደ ያዊ ድል ባጠገባቸው በሚገኙት በነደ ኮቪልሐእ ፤ በነአልቫሬጽ እየተሰበኩ ለጠቅላላ ድል የሚያመራ አድርገው የተመለከቱት ይመስላል ።

የሆነ ሆኖ እስላሞቹ በርከት ብለው በሚገኙባቸው የወደብ ከተሞችና ደሴቶች በምጥዋ በዳህላቅ በዘይላ የፖርቱጋል ወታደር እንዲሠፍርበት ማሳሰባቸው በርሳቸው ዘንድ በምክር የተወሰነ የዘዴ እርምጃ ይመስላል ። እነዚህን ወደቦች እራሳቸው ነዋሪ ወታደር አስቀምጠው በቀጥታ መቆጣጠር ሳይቻላቸው ስለቀረ በባ

(1) እዚህ ላይ ዣን ቴምፖራል የተረጐመው በፋርሲም ይለያያል የርሱ አነጋገር እንደዚህ የሚል ነው
"que je ne suis point ignorant de bon accueil que tu a fait à Mathieu mon ambassadeur de la grâce spéciale et Royale tu l'as défrayé de tout son voyage. . . . . . ለመላ
ክተኛዬ ለማቴዎስ ያደረግኸውን መልካም አቀባበል በልዩና በንጉሣዊ ቸርነትህ (ወይም ጸጋህ)
የጉዞውን ኪሣራ ሁሉ ከፈልህለት (ወይም ነፃ አደረግኸው ?) . . . . . . ። የአቶ በሻህ ወደ አማ
ርኛ አተረጓጐምና የሎርድ ስታንለይ ወደ እንግሊዝኛ አተረጓጐም ይቀራረባል ። ሁለቱም መላክ
ተኛውን "አብርሃም" ብለውታል ። አቶ በሻህ "ይህ ለኔ የተደረገልኝ ውለታ ለአብርሃም እንደ
ተደረገለት ይቆጠራል" ሲሉ ስታንሌይ "I send this to you knowing your virtue and
goodness, because I now well you love me, and also you did good to Abraham."
ይኸን (መልእክት) መላኬ የርስዎን ደግነትና በጎ ምግባር ስለማውቅ ምን ያህል እንደሚወዱኝ
ስለተረዳሁት ለአብርሃምም ደግሞ ብዙ ደግ ነገር ስለ አደረጉለት . . . ። ኢትዮጵያ ፖርቱጊዞች
እንዳዩዋት 377 - 383 ። "Portuguese Embassy to Abyssinia. Cap. VII - pages 389-
396. Deuxième partie du second Tome de l'Afrique page 247-252."

ሕር ግዶ ያሉት ቱርኮችና ዓረቦች በወዲህ ካሉት የዳህላቅና የምጥዋ የአዳል እስላ ሞች ጋር እየተገናኙ በርሳቸውና በመንግሥታቸው ላይ ጉዳት ባለፈው እንዳመጡ ባቸው ወደፊትም እንደሚያመጡባቸው በመገንዘብ ይኸን አስጊ ቦታ የቱርክን ኃይል ይመልሳል ብለው በገመቱት በፖርቱጋል እጅ አሲዘው የጦርነት ማጣ ቢመጣ ራሱ ችሎ ይመክታል ወይም በኅብረት እንመልሳለን ብለው ተመኝተዋል ማለት ነው ። ዳሩ ግን ወደፊት ባለው ጊዜ ውስጥ የፖርቱጋል ንጉሥ በሌላው ክፍለ ዓለም በአፍሪካ ፤ በኮንጎ ፤ በምሥራቅ በሕንድ ፤ በደቡብ አሜሪካ በብራዚል ያለበት ያገዛዝና የንግድ ጉዳይ እንደዚሁም በአውሮፓ ራሱን በቀጥታ የሚ መለከተው ሁኔታ ጊዜ አልሰጠው ስለአለ ይህ ሐሳብ ወደ ፍጻሜ ሳይደርስ ወደቦ ቹን ቱርኮች መልሰው ይዘው እርሳቸውንም ለብቻቸው በዓረቦች የተደገፈው ግራኝ አህመድ በጦርነት ያጣድፋቸው ገ‌ባ መር ።

በመጨረሻ በዚህ ደብዳቤ ላይ የፍቅራቸውን የቃል ኪዳን ልጅነታቸውን ለሽ ማግሌው ለአማኑኤል በመግለጽ ደብዳቤያቸውን ከመዝጋታቸው በፊት የወርቅና የብር ፤ የብረታ ብረት የማተሚያ ሥራ የሚያውቁ የእጅ ብልሃተኞች እንዲልክላ ችው በጥብቅ አሳስበዋል ። ይኸም እላይ በተባለው ምክንያት አልተፈጸመም ።

እነዚህኑ ሰዎች በኢትዮጵያ በሚቆዩበት ጊዜ ደመወዛቸውን ከመስጠት ጋር በመልካም እንደሚይዟቸው ወደ አገራቸው ለመመለስ በፈቀዱበትም ጊዜ ያለ ምንም ችግር እንደሚያሰናብቷቸው ቃላቸውን በመሐላ አጽንተዋል ። መሐላ የተ ጨመረበት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገባ የውጪ አገር ተወላጅ በዋዛ አይወ ጣም ። ንጉሡ እንደ መያዣ እያደረጉ አስገድደው ባገራቸው ያስቀሩታል የሚል ሐሜታ በፈረንጅ አገር በተለይ በፖርቱጋል አገር በዚህ ዘመን በርክቶ ተወርቶ የነ በረውን ለማስተባበል ነው ።

ISIC

ለምሳሌ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በመጽሐፉ የአበሾቹን ቋንቋ አጥርቶ ያው ቃል የሚባለው ብራንካ ሊዎንንና ይኸ ደብዳቤ ሲዘጋጅ ከግዕዝ ወደ ፖርቱጋል ያስተረጉምላቸው የነበረው ፔድሮ ደ ኮቪልሐእ ከዮሐንስ ፪ኛ ዘንድ ተልኮ ባዔ እስ ክንድር ዘመን ከመጣ በኋላ ወደ አገሩ እንዳይመለስ እንደመያዣ ሆኖ በኢትዮጵያ ከ፴ ዓመት በላይ በግዴታ መቀመጡን ጠቅሶታል (1) ።

ስለዚህ ዓፄ ልብነ ድንግል አገራቸውን ለማሠልጠን እነዚህን አዋቂዎች ቢጠ ይቁ አዋቂዎቹ ያስቀሩናል በሚል ሥጋት እምቢ እንዳይሉ ወይም ንጉሡ ራሱ ለዜጎቹ ሕይወት እንዳይሠጋ ሲሉ ባለሙያዎቹን እንዳያስቀሩ ቃላቸውን በመሐላ ሰጡ ማለት ነው ። ዳሩ ግን ወደፊት እንደምናየው በየወደቡም የፖርቱጋ ልን ወታደር የማስፈሩ ፡ አዋቂዎቹንም አስመጥቶ በእጅ ሥራ አገሪቱን የማሠል ጠኑ ጉዳይ እላይ እንዳመለከትነው ሳይታሰብ ተጣድፎ በደረሰው በግራኝ አህመድ ወረራ ተዋጠ ። እንደዚሁም ላባትነት የተመኙት ንጉሥ አማኑኤል መልክተኞቹ ከኢትዮጵያ ገና ሳይነሡ የተጻፈለትንም ደብዳቤ ሳይመለከት በዚሁ ዓመት ስለ ሞተ ምንም እንኳን በዙፋኑ የገዛ ልጁ ዮሐንስ ፫ኛ ቢተካ ዓፄ ልብነ ድንግል በን

(1) የአልቫሬጽ መጽሐፍ ምዕ. 104 ። የሐበሻ ታሪክ ጕንና ጥንርዮ የጻፉት ገጽ 88 ፤

ጉሥ አማኑኤል ላይ የጣሉት አለኝታና ተስፋ በገማሽ ከተዘቀዘ በኋላ ግንኙነታቸውን ከልጁ ጋር ወጠኑ ።

## ምዕራፍ ፳፯
## ስለ ንጉሥ አማኑኤል ዕረፍት - ለዮሐንስ ፫ኛ የተጻፈው ደብዳቤ ።

በዚህ ዓይነት ለንጉሡ ለአማኑኤል የሚሰጠውን ዘውድና ደብዳቤ ይዘው ለጉዞዎ ማናቸውም የጭን ከብትና የጭነት አጋሠሥ ስንቅም ከተሰጣቸው በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከመካከላቸው ፖርቱጋሎቹ (PHYSICOMESTERE JOA) የሚሉት የሕክምና መምህር ዮሐንስ ቤርሙዴዝና ሠዓሊው ላዛሮ ዴአንድራዴ (LAZARO) የሚባሉት ሲቀሩ ሁሉም መልክተኞቹ ማክሰኞ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፭፻፳፭ ዓ.ም. (እ. አ. ቀ.) ለመሄድ ተነሡ ።

እንደ አልቫሬዝ አነጋገር ዶም ሮድሪግ ባንድ ወገን የራሱን ሰዎች እያጉላላ ይበድላል የሚሉ ወሬ ስለተሰማ በዚህም ላይ ከገርጅ ደ. አብረው ጋር ከተጣሉ ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱ ታረቁና በሰላም እንደ አማረባችሁ ወዳገራችሁ ተመለሱ ብለው ቢለምኑት እምቢታውን ስለአጸና ንጉሡ ቅርታ ስለተሰማቸው በመልእክት እንጂ ከፊታቸው ቀርቦ እጅ ነሥቶ የመሰናበት ዕድል አልሰጡትም (1) ። በዚህ ላይ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ በፊት ለረዥም ቀን ደጅ በማስጠናታቸው ያሳዩትን ጉድለት እርሱ ደግሞ የመልክተኞቹ መሪ እንደመሆኑ መጠን ተስማምቶ ወገኖቹን ማስማማት ሲገባው በዚህ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ታረቅ ሲሉት አልታረቅም ብሎ የግትርነት ጠባይ ማሳየቱ ለተጣለበት የመልእክት ሹመት የማይመጥን መሆኑን ያሳያል ። ከርሱ ይልቅ ብልህነት ፣ ለዘብታ በካህኑ በአልቫሬዝ ላይ ይታያል ።

የሆነ ሆኖ ያንድ አገር የፖርቱጋል ተወላጅ የሆኑት ሁለቱ ጠበኞች ለየብቻ ሆነው ተራርቀው መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ተሰናብተው የተነሡት መካነ ሥላሴ ከሚገኙበት ከቤተ አምሐራ (ዛሬ ወሎ) ስለነበረ በላስታና በአንጎት ፣ በትግሬ በኩል አድርገው ሲጓዙ ከነርሱም ጋር ሆነው አንዳንድ ጊዜ እየቀየሙ አዳርና መስተንግዶ በማዘጋጀት ይረዷቸው የነበሩት ራሱ መላክተኛው አባ ጸጋ ዘአብ ፣ የልፍኝ አሽከሮች አለቃ አብዲናጎና የዓቃቤ ሰዓቱ ልጅ ስለነበሩ ፖርቱጋሎቹ በየመንገዱ እርስ በርሳቸው እየተጣሉ በራሳቸው ከመቸገራቸው በቀር በማናቸውም የስንቅ ችግር ሳይገጥማቸው ወደ ባሕር ነጋሽ ከተማ ወደ ደባርዋ ደርሰው የመርከብ ወሬ እየተጠያየቁ ይጠብቁ ጀመር ።

ነገር ግን ባንድ ወገን መርከቡ ስለአልተገኘ ቀጥሎም ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጣቸው ስጦታና ስንቅ የተነሳ የርስ በርስ ጠባቸው እየጋለ ስለሄደ እንዲሸኟቸውና እንዲያስተናግዷቸው የታዘዙት ባሕር ነጋሽ ዮሬ ፣ ራስ ነቢያትና ሕዱግ

(1) ምዕ. 106



ሮድሪጎ ደ ሊማ በጉዞ ላይ (VIAGENS-COVILHAO)

ISIC

ራስ (ማኅፀንቶ) ተመካክረው ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት ወደ ሸዋ እንደገና መለሱዋቸው ። ከዚህ በኋላ ነው የንጉሡን አጀብ ተከትለው ጉራጌን ጐብኝተው ዓቢይ ጾምንና ፋሲካን በዚሁ አገር ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ያሳለፉት ።

በዚህ ጊዜ እነሱ ከደባርዋ ተመልሰው በጉራጌ አገር ፋሲካን ካሳለፉ በኋላ የንግሥት ናዖድ ሞገሳ ሙት ዓመት ተዝካር በሚከበርበት ሰዓት ዶም ሉዊዝ ደ ሜኔዜስ ( DOM LUIZ DE MENEZES ) የሚባለው እነርሱን ለመውሰድ ምጥዋ ወደብ ገብቶ ኖሮ ከዋናው የሕንድ ገዥ ከዲዩጎ ሎፔዝ የተላከ አንድ ደብዳቤና ያገር ካርታ ለንጉሠ ነገሥቱ ሁለተኛው ደብዳቤ ለነርሱ የተጻፈ ደረሳቸው ። ለንጉሡየተጻፈው ፖርቱጋሎቹን እንዲያሰናብቷቸው የሚያመለክት ሲሆን ለራሳቸው ከደ መኔዝስ የተጻፈው ደግሞ የክረምቱ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ወደ ምጥዋ በ፲፭ ቀን ውስጥ እንዲደርሱ እርሱም በሕንድ ስለሚፈለግ በቶሎ ለመመለስ ግዴታው መሆኑን ከማሳሰብ ጋር የንጉሡን የአማኑኤልን ሞት ያረዳል ።

መልክተኞቹም የንጉሣቸውን ሞት ሲሰሙ ታላቅ ኀዘንና ድንጋጤ አደረባቸው ። ወሬውንም በአልቫሬጽ መጽሐፍ ላይ እንደተባለው ከአፄ ልብነ ድንግል ደብቀው በቶሎ ወዳገራቸው ለመመለስ አስበው ነበር ። ነገር ግን እኛ ደብቀን ንጉሡ ወደ ዓረብ አገር በሚመላለሱት ነጋዴዎች አማካይነት መስማታቸው አይቀርምና እኛው ብንናገር ይሻላል ተባብለው ላፄ ልብነ ድንግል ገለጹላቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም በበኩላቸው በደብዳቤያቸው ላይ እንደ[illegible]ነው አማኑኤልን እንዳባት በመቁጠር ተመክተውበት የነበረ የወዳጅ አገር ንጉሥ በመሆኑ አዝነው ስለሟቹ ንጉሥ የ፲ ቀን የኀዘን ዕረፍት ሆኖ በሙሉ በአዋጅ መሥሪያ ቤቶቹና ሱቆቹ ሁሉ ተዘጉ ። ፖርቱጋሎቹም እንግዲህ ንጉሣችን ከሞተ ያለጠባቂ በሰው አገር ጠፍተን ቀረን የሚል የተስፋ መቁረጥ ስሜት አድሮባቸው ኖሮ ንጉሡ አይዟችሁ ያላችሁት በክርስቲያን አገር ነው ፤ አትፍሩ ብለው አጽናንተው መርከቡ ትቷቸው እንዳይሄድ ዮሐንስ ጎንዛልቬስ (JOA CONCALVES) በቅድሚያ ወደ ምጥዋ ሄዶ ከሉዊዝ ደ ሜኔዚስ ጋር እንዲገናኝና እንዲያቆየው ላኩት (1) ። ከዚህ በኋላ እንደገና ለሁሉም የወርቅ ስጦታ የልብስ ሽልማት ሸልመው በማናቸውም አስደስተው ከዚህ በፊት ስማቸውን የጠቀስነውን ቤርሙዴዝንና ላዛሮን ሁለቱን ብቻ ሲያስቀሩ የቀሩትን መልሰው ወደ ጠረፍ ላኩዋቸውና ጉዟቸውን ገሠገሡ ። ዳሩ ግን በመንገድ ላሉ ወደ ጠረፍ ተልከው ከነበሩት ውስጥ ተመልሰው ወደነሱ ሲመጡ በመንገድ አገኙዋቸውና ሉዊዝ ደ መኔዚስና መርከቡ ጠብቆ ካጣቸው በኋላ ተመልሶ መሄዱን ፤ ካንድ ዓመት በኋላ የሚመለስና በተመለሰም ጊዜ ሁለተኛ እንዳያጣቸው ማስጠንቀቁን ገለጹላቸው ። ቢሆንም አንድ ጊዜ እዚህ ከደረስን በማለት ወደ ምጥዋ ሄደው ሉዊዝ የተወላቸውን አንዳንድ ዕቃና የበርበሬ ጥቅል አግኝተው

(1) ምዕራፍ 112 - 114

አሁንም እንደገና ከምጥዋ ንጉሡ ወዳሉበት ወደ ፈጠጋር (እ. አ. ቆ.) ፲፭፴፩ ዓ. ም. በኅዳር ወር ተመልሰው መጥተው ለንጉሡ የሆነውን ሁሉ ነገሯቸው ፤

በዚህ ጊዜ እንደገና በፖርቱጋሎች ከዚያም በአልቫሬጽ ምክር ሳይሆን አይቀርም ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ሰባተኛ (CLEMENT VII) እንዲሁም ለአማኑኤል ልጅ ለዮሐንስ ደብዳቤ ይጻፍ ተብሎ እንዳለፈው ስለ እጸፉ ፤ ስለ እርእስቱ ተመክሮ ተዘክሮ ተጽፎ ካለቀ በኋላ ለንጉሡ የሚሰጠውን ደብዳቤና ገጸ በረከት ሊቀ ካህናት ጸጋ ዘአብ ፤ ለሊቀ ጳጳሱ የተጻፈውን ደብዳቤና ገጸ በረከት ፍራንቸስኮ አልቫሬጽ እንዲያደርሱ ተነግሯቸው ፡ አሁንም መርከቡ እንዳያመልጣቸው እዚያው ሄዶ መጠበቅ ይሻላል ተብሎ ሁሉንም መልሰው ከላኩዋቸው በኋላ በእርትራ ላሉ ሥራ ፈትተው መርከብ በሚጠብቁበት ጊዜ ከደባርዋ ወደ አክሱም ብዙ ጊዜ እየተመላለሱ አገር ሲጐበኙ ቆይተው በመካከሉ እምባሳደር ሆኖ ሊሄድ የታዘዘው አባ ጸጋ ዘአብ ከግዛቱ አንዱን ወረዳ አብዲናን ቀምቶኛልና ወደ ንጉሡ ነሥቱ ተመልሼ አቤት እላለሁና እርስዎም ከእ ጋር ተመልሰው በማመልከት ይረዱኛል ብሎ ከአልቫሬጽ ጋር እንደገና ወደ ሸዋ እንደ ጊዜ እንደተመለሰ ይኸው አልቫሬጽ ይጽፋል (1) ።

የሆነ ሆኖ በዚህ ዓይነት ውጣ ውረድና መመላለስ መርከብ ጥበቃና ዝግጅት በድምሩ የ፮ ዓመታት ጊዜ (፲፭፻፳-፳፮) በኢትዮጵያ ከሳለፉ በኋላ በመጨረሻ ሁሉም ጥዋ ተሳፍረው ወደ ካምራን ደሴት ከካምራን በሖርሙዝ አድርገው ወደ ሕንድ ዳቡ አስረክበው እንደቆዩ እ. አ. ቆ. በ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ጥር ፲፰ ቀን ከሳእ ጉዟቸ ውን ቀጥለው በዚሁ ዓመት በሐምሌ ፳፬ ቀን ሊስቦን ገብተው ያንኑ ለአማኑኤል ፫ኛ የተጻፈውን ጭምር አምባሳደሩ ጸጋ ዘአብ አቅርቦ "...... ጊታዬ ዓፄ ልብነ ድንግል ይኸን ዘውድና ደብዳቤ የላኩት ላባትዎ ለንጉሥ አማኑኤል ነበር ነገር ግን የንጉሥ አማኑኤልን ሞት በሰሙ ጊዜ ላባቱ ለንጉሥ አማኑኤል የተመደበው ዘውድና ደብዳቤ ለንጉሥ ዮሐንስ ይሰጥ" ብለዋል ብሎ መናገሩን አልቫሬጽ በመጽሐፉ በ፪ኛው ክፍል ምዕራፍ ፮ ላይ ገልጿል ። ከዚሁም እያያዘ በበኩሉ ንጉሡ ዮሐንስ ሁለት መነኰሳት ፫ በቅሎዎች የወር ቀለብም ቤትም ማናቸውንም አስፈላጊ ዕቃ ከሁለት አሽከሮች ጋር አዞ ደህና መስተንግዶ እንዲደረግላቸው መታዘዙን በዚሁ ምዕራፍ ላይ አብራርቶ ጽፏል ።

እንደዚያው እንደፈተኛው ዓፄ ልብነ ድንግል ላዲሱ የፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ ሃይማኖትን ፖለቲካን የተደገፈ ረዘም ያለ ደብዳቤ ስለ ሆነ በሙሉ መጻፍ አንባቢን እንዳያሰለች በተለምዶ የተጻፈውን መንፈሳዊ አነጋ

(1) ምዕራፍ 117

ISIC




ዓፄ ልብነ ድንግል ደብዳቤ የጻፉለት ዮሐንስ ሳልሣዊ በቤተ ክርስቲያን ሲጸልይ (ከፖርቱ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር)

ገር ትቼ ታሪክና ፖለቲካ ነክ የሆነውን በመምረጥ ከዚህ በታች ጽፌዋለሁ ። ከዚህ በታች ያለው ከዣን ቴምፖራል መጽሐፍ ላይ የተገኘ ሲሆን ከአልቫሬዝ ጽሑፍ እነአቶ በሻህ ከተረጐሙት ጋር በጠቅላላው በመሠረቱ አንድ ሆኖ አንዳንድ ቦታ ላይ በጥቃቅን ጉዳይ መለያየቱን ለአንባቢ አስገነዝባለሁ ። እንደዚሁም በቅርብ ጊዜ በሸዋ ከዚይ ደሴት ቄስ ገበዝ ተክለ ሃይማኖት ወልደ ኪዳን ያገኙት የቀናው የግዕዙ የደብዳቤ ግልባጭ በመጨረሻ ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ በ፫ኛ ስ፩ ኛው የኢትዮጵያ ጥናት ጉባዔ ያቀረቡት ለግዕዝ ዓዋቂዎች በሙሉ ከዚሁ ግርጌ በረቂቅ ፊደል ታትሟል (1) ።

(1) «በስመ እግዚአብሔር አብ እጋዜ ዙሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ወዙሉ ፍጥረታተ ዘያስተርኢ ወዘ ኢያስተርኢ ። ወበስመ እግዚአብሔር ወልድ ፈቃዱ ወምክሩ ወነቢዩ ለአብ ። ወበስመ እግዚአብ ሔር ወመንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ እግዚአብሔር ሕያው ዕሩይ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በል ሳነ ነቢያቲሁ ወወረደ በላዕለ ሐዋርያት ወይሴብሕዎ ወየአዙትዎ ለቅድስት ሥላሴ በሰማይ ወበ ምድር በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

ዘንተ መልእክተ ወሐዋርያ ይፌኑ ንጉሥነ ልብነ ድንግል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወልዱ ለና ዖድ ወልደ ንጉሥ በእደ ማርያም ፤ ወልደ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ወእምዘርዓ ዳዊት ወሰሎሞን እለ ነግሡ በኢየሩሳሌም ። ዛቲ መልእክት ትብጻሕ ኀበ አቡቶሁ ዮሐንስ ንጉሠ ብርቱጓል ወልደ ንጉሥ አማኑኤል ሰላም ለክሙ እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ የሃሉ ምስሌክሙ በዙሉ ጊዜ ። ሶበ ሰማዕነ ዜና በእንተ ኃይለ መንግሥቱ ለአቡክሙ ዘአድከመ ባቲ መንግሥቶሙ ለደቂቀ መሐመድ . . . . . እእኵትናሁ ለእግዚአብሔር እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ዘአንሐ አክሊለ መድኀኒቱ ላዕለ ቤተ ውሉደ ጥምቀት በእንተ ዝንቱ ተፈሣሕነ ጥቀ ሶበ በጽሐ ኀቤነ ቃለ ሐዋር ያሁ ዘይቤ ከመ ንትፋቀር በበይናቲነ ወናጠፍአሙ እመንግሥቱ ወእመንግሥትነ ለደቂቀ መሐ መድ ወለአይሁድ ወለአሕዛብኒ ። ወእንዘ ሀሎነ በዛቲ ፍሥሐ ዙነውነ በእንተ አቡክሙ እመፈ ለሰ እምዝንቱ ዓለም እምቅድመ ንፈኑ ንሕነ ሐዋርያቲሁ ዘበጽሑ ኀቤነ ። ወበእንተዝ ሀየንተ ፍሥሐ ዘቀዳሚ ረከበነ ትካዝ ፈድፋደ በውስተ ልብነ እንዘ ንዜክር ፍልሰቶ ወዙሉ ዓበይተ ሰብእ ቤትነ ወለሐዉ ዓቢየ ላሐ ዘመጠነዝ ። ተመይጠ ፍሥሐሆሙ ዘቀዳሚ ኀበ ኀዘን ። አ እግዚእየ ወእኅየ ወእምድኅረ አንገሠኒ እግዚአብሔር እስከ ዮም ኢመጽአ ኀቤነ ሐዋርያ እምክርስቶሳው ያን ነገሥተ ብርቱጓል ። ባሕቱ ሰማዕነ ከመ ሕዝብክሙ ሀሎ በብዙኅ ኀዐር ወምንዳቤ በፈቃዶሙ የሐውሩ ለሐውፆ ሀገረ ሮምያ ቅድስት ወሀገረ ኢየሩሳሌም ኅሪት ። ወዛቲ ጽድቅኒ ኢሰማዕነ ዘእን በለ በመዋዕሊሁ ለአቡክሙ ዘፈነዉ ኀቤነ እመላእክት ወእም ዓበይተ ቤቶሙ ቀሲሳነ ወዲያቆናተ ኖሙ በዓቢይ ትፍሥሕት ወክብር ወፍሥሐ ። ፈነውናሙ ዳግመ ኀቤሁ ወሶበ በጽሑ ኀበ ባሕረ ኤርትራ ፍጻሜሁ ለሀገረ መንግሥትነ ኢረከብዎ ለመልእክ ሀንድ እስመ ውእቱ ተመይጠ ኀበ ሚመቱ በእንተ ዘተፈጸመ ዕድሜሁ ዘሣልስ ዓመት በከመ ልማደ መንግሥትክሙ ወበእንተዝ ጕንደዩ ኀቤነ ። ወይእዜኒ ንፈንዎሙ ለክሙ ምስለ ሐዋርያነ ለእለ ፈነውነ አቡክሙ ኀበ አቡነ ከመ የሀቡክሙ መልእክትነ ለኀቤክሙ ወኀበ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮምያ ። እእግዚእየ ወእኁየ ፈጽሙ እስመ ደቂቀ መሐመድ . . . . ይትፋቀሩ በበይናቲሆሙ ። ንሕነስ ክርስቶሳውያን እሮ ያ.ደልወነ ከመ ንትፋቀር በበይናቲነ ። እምይእዜሰ ኢንፈቅድ ሐዋርያተ እምገብጽ ወእምኀልእንኒ ነገሥ ታት ዘለመዱ ይፈንዉ ኀቤነ ። ዳዕሙ ንፈቱ ሐዋርያክሙ ። ነገሥታተ መሐመድኒ ያፈቅሩነ በእ እስመ ከመዝ ገብሩ አበዊነ ነገሥታተ ኢትዮጵያ እብርሃ ወአጽብሐ ታዜና ካሌብ ገብረ መስቀል ቅቡዓነ አከሱም እስመ እሙንቱ ስምዕ ለዙሉ ። ወበትእዛዘ እሉ ኢትቅትትሎሙ ከመ ኢያመዝብሩ

"የሚታየውንና የማይታየውን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ የአብ ነቢይና መላክተኛ ልጁም በሆነ በእግዚአብሔር ወልድ ሐዋርያት ወንጌልን ይሰብኩ ዘንድ በአጽናና በነቢያት አፍ በተናገረ ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል በሆነ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሦስትነታቸው በሰማይም በምድርም ፡ በባሕርም ፍጹም በሆነው በሥላሴ ስም አሜን ።

እኔ ዕጣነ ድንግል ትርጓሜውም ድንግል ያበራችለት ይኸም ስም የተሰጠኝ ክርስትና በተነሣሁበት ቀን ነው (1) ። አሁን ግን በትረ መንግሥት በጨበጥሁ

መቃብሩ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሀሎ በኢየሩሳሌም ወካልእነኒ አብያተ ክርስቲያናት እለ ሀለዋን ሀየ ወበምድረ ግብጽ ። ባሕቱ ብነ ኀዘን በእንተ ዝንቱ ወበእንተ ዘአልብነ ንጉሠ ክርስቲያን ኀበ ዘይረድአነ ወያስተፌሥሐነ ። አ እግዚእየ ወእኁየ ነኀዝን ጥቀ በእንተ ነገሥታተ ኢየሮፓ በእንተ ዘይትበዓሉ በበይናቲሆሙ ብዙኀ ጊዜያተ በነገር ቀሊል ። ለእመ ብነ ንጉሠ ክርስቲያን ኀበ ኢንጸልዮ ግሙራ ። ምንተ እንከ ንብል እስመ ዘኢነአምር ለእመ ኮነ ዝንቱ በተበውሖ ለእግዚአብሔር ።

አ እግዚእየ ንጉሥ እኁየ ፈንዉ ለነ ሐዋርያተክሙ ወመልእክተክሙ በኵሉ ጊዜ እስመ ንፈትዎሙ ፈድፋደ እምነ ርዕየተ መዛግብቲነ ። ወናፈቅሮሙ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በከመ ይቤለሊሁ ኀበ ሀሎ መዝገብከ ሀየ ሀሎ ልብከ ። አንትሙሰ መዝገብነ አንትሙ ። ወከመዝ ስምዑነ ወአስተጋብኡ ልብነ ምስለ ልብክሙ ። አ እግዚእየ እኁየ ዕቀቡ በልብክሙ ዘንተ ቃለነ እስመ ሰማዕነ ከመ ትጠበቡ እምነ እቡክሙ ፈድፋደ ። ወነአኵቶ ለእግዚአብሔር በእንተ ዝንቱ ወኀደግነ ትካዜነ ወተፈሣሕነ እንዘ ንብል ብሩክ ይኩን ወ[illegible]ጠቢብ ንጉሥ እቤቶሁ አማኑኤል ዘይነብር በመንበረ መንግሥቱ ። አ እግዚእየ ሰብዑ ወኢትድክሙ ለተቃትሎ ወለአጥፍኦ ኢአማናውያን ወኢትብሉ አልብነ ኀይል እስመ እግዚአብሔር ይረድአክሙ ። ለነሰ ብነ ወርቅ ወኵናት ወሲሳይ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ወከመ ኆፃ ባሕር ባሕቱ እመ ኀበርነ ክልኤነ ንመውዖ ለኵሉ ዓለም ። ንሕነሰ ኢንፈቱ እምኔክሙ ዘእንበለ ዕደው ጽኑዓን እለ ይመልኩ ወይሠርዑ ሰብአ ዘእነ በኵናት ። አንትሙሰ ብእሲ ፍጹም አንትሙ ከመ ሰሎሞን ንጉሥ ዘነግሠ አርብዓ ዓመተ ወኀየለ ወጠበበ ፈድፋደ እምአቡሁ (እንሰ ። ?)

እመ ጊዜ ፈለሰ አቡየ ንጉሥ ናዖድ እምዝንቱ ዓለም ንዑስ ንሕነ ነገሥነ ሀየንቴሁ ወእግዚአብሔር ወሀበነ ኀይለ ፈድፋደ እምኔሁ ወንቀኒ ባሕቱ ሕዝበነ በሰላም በእንተ ዝንቱ ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ። አ እግዚእየ እኁየ አጽምዑ ዳግመ ቃለነ ። ንሕነኒ ንፈቱ ከመ ታጽምዑ ወትፈንዉ ኀቤነ ሰአልያነ ምስለ ወጠቢባን ማኅተመ መጻሕፍት ወመሀርያነ ግብረ ጥበብ ወዓቃብያነ ሥራይ ወሐናፅያነ ቤት ወጠቢባን እለ የአምሩ ገቢረ አውጽኦ ወርቅ ወብሩር ወዓረር ። ወካልአንሂ ጠቢባን ዘያስተሠንዩ ለመንግሥትነ ። ተራድኡነ በዘንስእለክሙ ከመ ይትራዳእ እኁ ለእኁ ወእግዚእየ ይርዳእክሙ እምእኩይ ።

እግዚአ እግዚእነ ይትወከፍ ጸሎትክሙ በከመ ተወክፈ መሥዋዕቶሙ ለጻድቃኒሁ በኵሉ መዋዕለ ዓለም ዘውእቶሙ አቤል ኖኅ አብርሃም ወለካልአንሂ ጻድቃን ከማሁ ይትወከፍ እግዚአብሔር መሥዋዕተክሙ ወጸሎተክሙ ወይርዳእክሙ ከመ ታድኅኑ ፀረክሙ በኵሉ መዋዕል ። ሰላም ለክሙ ንሕነኒ ነሐቅፈክሙ በመዝራዕት ምሉአ ጽድቅ ። ወዓዲ ንትዌከፈክሙ ወንትዌከፎሙ ለመማክርተ ዐበይተ መንግሥትክሙ ወለሊቃነ ጳጳሳት ወጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ለኵሎሙ ዕድ ወአንስት ። ጸጋሁ ለእግዚአብሔር ወበረከታ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ወበረከተ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕታት ወጻድቃን ለዓለመ ዓለም የሀሉ ምስሌክሙ አሜን ወአሜን ።»

በግዕዙ ጽሑፍና በፈረንሳዊው ትርጉም መካከል ያለው ልዩነት ጥቃቅን መሆኑን አንባቢ እያገናዘበ ሊረዳው ይችላል ። የግዕዙ ደብዳቤ ግልባጭ መገኘትም በታሪክ ፊት ከፍተኛ ዋጋ አለው ።

(1) ዕጣነ ድንግል ያለው ያንኑ ልብነ ድንግልን በመተርጐም መሆን አለበት ፣

ጊዜ የፍቁረ እግዚእን የዳዊትን ስም የሃይማኖት ዓምድ ከይሁዳ ቤት የመጣውን ወሰድሁ ። የጃኤል ነገሥታት የዳዊት የሰሎሞን ልጅ የዓምደ ጽዮን የዘርዓ ያዕቆብ የበእደ ማርያም የናዖድ ልጅ በሥጋ ልደት ። ለትልቁና ለኃያሉ መስፍን ለዶም ዮሐንስ የፖርቱጋልና የአልጋርቭ ንጉሥ የንጉሥ አማኑኤል ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ካንተ ጋር ይሁን አሜን (1) ።

ያባትህን ችሎቱንና ኃይሉን ሰምቼ ለሕያው እግዚአብሔር ምሥጋና አቀረብሁ ። እኔም ለዚሁ ጉዳይ ኃይሉን ሁሉ ለመጨመር ሁል ጊዜ እንደተዘጋጀሁ ነኝ ። አሁንም በኔና በአባትህ ጊዜ ተዠምሮ የነበረው ወዳጅነትና አንድነት ባንተም ጊዜ መጽደቁን ከአባትህ መልክተኞች በመስማቴ ከቀድሞው የበለጠ በደስታ ግያለሁ ። ስለዚህም እነዚህን በሁለታችንም የግዛት ጠረፍ ያሉትን እስላሞችና አይሁዶች ለመውጋት ማናቸውንም ዕርዳታ እሰጣለሁ ። በእንደዚህ ያለ መተሳሰብ በደስታ ባለሁበት ጊዜ የሚያሳዝነው ያባትህ ሞት ስለደረሰኝ ትልቁ ደስታዬ ወደ ኀዘን ተለውጦ አሳቤና ምኞቴ ሁሉ እንደገና እሥር ገብቶ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆነ ። ባገሬ ያሉት መኳንንትና ሊቃውንት በአብያተ ክርስቲያናትና በገዳማት የሚገኙት ሁሉ በጠቅላላው ዜጋችን በሆነው ላይ ሁሉ ይህ አደገኛ ጠራ መራራ ኀዘንንና ሰቆቃውን (ለቅሶ - ዋይታ) ጣለበት ። ለኔም ለራሴ ከነገሥሁበት ቀን ዠምሮ መልክተኛና ደብዳቤ የተላላክሁት የክርስቲያን ንጉሥ እርሱ (አማኑኤል) ብቻ ስለነበረ በርሱ ክፉኛ ሞት ልቤ ከልክ ያለፈ አዝኗል ። ከርሱ ዘንድ ተልከው ወደኔ የመጡት ጕበዛዝት ካህናት ወደኔ አገር በመጡና የቤተ ክህነቱ ወገኖች ቅዳሴያቸውን አሳምረው በአሳዩኝ ጊዜ በሥርዓታቸው ደስ አለኝ ። እኔም በመጡ ጊዜ አክብሬ በቤተ መንግሥቴ ተቀብዬ ስጦታም አድርጌ ወደ አገራቸው በሚመለሱበትም ጊዜ የይለፍ ወረቀት ሰጥቼ አሰናበትኋቸው ። ዳሩ ግን እቀይ ባሕር ዳር እግዛቴ ጠረፍ ሆነው ሲጠባበቁ አባትህ አዞላቸው የነበረው ዋናው የጦር አለቃ ሳይመጣላቸው ቀረና በዚሁ ብዙ ጊዜ ኖረው ተመለሱ ። እኔም ወዲያው መላክተኛዬን (ሊቀ ካህናት ጸጋ ዘአብን) ምኞቴን ሁሉ እንዲገልጽልህ ወዳንተ ልኬ በዚሁም ጊዜ ታዛዥነቴን ለመግለጽ ወደ አባታችን ወደ ሊቀ ጳጳሱ (ሮማ) ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን ላክሁት ።

ጌታውና ንጉሡ ወንድም ሆይ ከሚቻ አባትህ ዠምሮ በመካከላችን ስለተመሠረተው ወዳጅነትና መረዳዳት የምነግርህን ስማኝ ። ከአባትህ ግንኙነት ከጀመርን አንሥቶ መላክተኞችም ደብዳቤም እየመጣልኝ ልክ ከወንድሜ ዘንድ እንደመጣልኝ እየተመለከትሁ ደብዳቤውን አነበው ነበር . . . . . ። ይልቁንም ሁለታችንም ክርስቲያን በመሆናችን ይቺን ሃይማኖታችንን ለመከላከል የሁለታችን ዝምድና አስፈላጊ ነው ። ወደፊት ከግብጽ ንጉሥም ከሌላውም አምባሳደርም መላክተኛም እንዳልቀበል እምልልሃለሁ ። አንተን ግርማዊነትህን ደስ የሚያሰኙትን መልክተኞችህን ብቻ እቀበላለሁ ። ከሃይማኖታችን ስለማይገጥም ከነዚህ ነገሥ

(1) የአልጋርቭ ንጉሥ የሚል ቃል በሎርድ ስታንሊይ ትርጉም ውስጥ የለም ። ገጽ 396

ታት ጋር ቃል ኪዳንም ወዳጅነትም የለኝም ። ወዳጆቼ ቢመስሉም ይኸን ወዳጅነት አመኳኝተው በግዛቱ የሚገኘውን ብዙ ወርቅ በያመቱ እያመላለሱ ለመውሰድ ሲሉ ነው ። ይኸንንም ሲያደርጉ ከኔ በፊት ከነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ተለይቼ የመግቢያና የመውጫ ፈቃድ ሳልከለክላቸው መቅረቴ በዚህ ተናደው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር የሚገኝበትን የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ያቃጥሉታል ብዬ ፈርቼ ነው ። የነሱም የዘወትር አሳባቸውና ምኞታቸው በግብጽም በሶርያም የሚገኘውን ቅዱስ ቦታ ለመዝረፍ ነው ። ጌታው ወዳጄ ሆይ ከአውሮፓ የክርስቲያን ነገሥታት ጋር እስካሁን ተዋውቄ በነሱ ልጽናና አልቻልሁም ። እነሱም እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ትልቅ ጦርነት ያደርጋሉ ። ደግሞ ይበልጥ የሚገዝነው ከነዚህ ከአውሮፓ የክርስቲያን ነገሥታት ጋር መራራቃችን ነው ። በግዛቴ ወሰን አንድ የክርስቲያን ንጉሥ ቢኖር ኖሮ በደስታ ከርሱ ጋር በጓደኝነት እንኖር ነበር ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደዚህ ከሆነ ሁሉንም በትዕግሥት ማድረግ ይገባኛል ። ስለዚህ የቀረው ቢቀር ሁልጊዜ በደብዳቤህና በመላክተኛህ እንድትጐበኘኝ እለምንሃለሁ ። ደብዳቤዎችህንም ሳነብ እንዳየሁህ ያህል እቆጥራለሁ ። አንድ ወዳጅም በሩቅ ያለውን ወዳጁን ከቅርብ ካለው ይበልጥ እንደ ገንዘቡ አድርጎ ሁልጊዜ ያስበዋል ። ይኸም ጌታችን በወንጌሉ (ኀበ ሀሎ መዝገብከ ህየ ይሄሉ ልብከ) ገንዘብህ ወዳለበት ልብህ ወደዚያ ይሆናል እንዳለው ላንተ ያለኝ ፍቅር እንደዚሁ ነው ። ISIC

ወንድሜ ሆይ የምነግርህን ሁሉ አትዘንጋ ። እንደሰማሁት እንደሚቼ አባትህ አዋቂና ጥንቁቅ በመሆንህ ደስ ብሎኛል ። አባትህም በኔ ላይ የተወውን መልካም መታሰቢያ ሳስታውስ ኀዘኔ ይቀሰቀሳል ። አሁንም በግዛቱ መንበር የተቀመጠው ጠቢቡ የንጉሥ አማኑኤል ልጅ የተባረከ ይሁን እያልኩ ለአምላኬ ምሥጋና አቀርባለሁ ። በእግዚአብሔር እርዳታ እነዚህን እስላሞች ለመውጋት ወደኋላ እንዳትል እኔም በበኩሌ ሰውም ወርቅም ስንቅም በብዙ ለመስጠትና ለመርዳት ተስፋውን አረጋግጣለሁ ። ይኸም ሁሉ (ሰውና ወርቅ) በኔ ዘንድ እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተ ነው ። እንደዚህ አድርገን በቃል ኪዳን አሚልተን ከሠራን የማውሪታንያን አገር (ሰሜን አፍሪካ ?) በእጃችን ለማድረግ እንችላለን ። ከዚህ በላይ የምለምንህ ዜጋዎቼንና ቤተሰቦቼን የጦር ሥርዓትና የሰልፍ አጠባበቅ ደንብ የሚያስተምሩ የጦር ጥበብና ልምድ ያላቸውን ሰዎች እንድትልክልኝ ነው ። ያንተ ኃይል ብዙ ነው ። ዕድሜህም ከሰሎሞን የበለጠ ስለሆነ ጠንካራ ነህ ። ሰሎሞን ሲነግሥ ፲፱ ዓመቱ ነበር ነገር ግን ከአባቱ ይበልጥ ዝግንነትና ጥበብ ሠራ ። ሌላም ምሳሌ ደግሞ አባቴ (ናዖድ) ሲሞት እኔ ፲፩ ዓመቴ ነበር በእግዚአብሔር ዕርዳታ ከነገሥሁ ወዲህ በግዛቴ ወሰን ያሉትን አገሮችና መንግሥቶችንም አስገበርሁ ። ስለዚህ አንተንም እኔንም ለረዳን እግዚአብሔር ሁለታችንም ምሥጋና እናቅርብ ። ጌታና ወንድም ሆይ ሥዕል የሚሠሩ መጽሐፍ የሚያትሙ የጦር መሣሪያ የሚሠሩ ፕላን ሠሪ አናጢ የመቅደድንና የአካልን ባሕል የሚያውቁ ሐኪሞች (ቪሩርጊንና ፊዚሲያን) እንደዚሁም ወርቅን ፥ ብርን ፥ ብረታብረትን የሚያ

ወጡ የማዕድን ሠራተኞች ቅርጽ መቅረጽ የሚያውቁትን ይህና ይህና ሠራተኞች እንድትልክልኝ እለምንሃለሁ ። ይልቁንም እንጥረኞች ዕጡብ መሥራት የሚችሉ ላክልኝ ። በጠቅላላው ሁሉም ሠራተኛ በየዓይነቱ ያስፈልገኛል ። ለጊዜው በጣም የሚያስፈልገኝ ሐርከቡዝ (ረዥም የጥንት ጠመንጃ) ታላላቅ መድፍ የሚሠሩ ሠራተኞች ናቸው ።

ወንድም ወንድሙን ሊረዳው እንደሚችል አንተም በማናቸውም ነገር እርዳኝ ። የእግዚአብሔር ሰላም ሁል ጊዜ ካንተ ጋር ይሁን ። በቅድስና በፍቅር ካንድ ስሜ እሳለምሃለሁ . . . .» (1) ።

በደብዳቤው የሠፈሩት ቃላት ሲነበቡ ዓፄ ልብነ ድንግል በፍጹም ልብ አገራቸውን ፣ ሕዝባቸውን በየመስመሩ ለማሠልጠን ቆርጠው የተነሡ መስለው ይታያሉ ። በአድራጎት የሚፈጽሙትና ያገራቱና የመንግሥቱ ድርጅት ከዚህ በፊት ያነበብነው ሲገመት ሁኔታው በደብዳቤዎቹ ላይ ከሠፈሩት አሳቦች ጋር ይራራቃል ። በዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን በደብዳቤው ላይ የሠፈሩትን ቃላት በዚህ ዓይነት እንዲሳካ ያደረጉ እንደልማዳቸው አዋቂዎቹና ራሳቸው እንአልቫሬጽ ናቸው ። ሲጽፉም ጠቅላላውን የንጉሡን ምኞትና አሳብ መጠየቃቸው ባይቀርም አጻጻፉ ግን ዮሐንስን ሊያስደስት በሚችለው መንገድ ያዘጋጁት ጸሐፊዎቹ ስለሆኑ ሥራና የሩቅ ምኞት የተገናዘቡ አይመስልም ። የሆነ ሆኖ በቀጥታ በግዕዙ የተጻፈውም ደብዳቤ ከፍራንቼስኮ አልቫሬጽ መጽሐፍ ላይ የተተረጐመውም እንደሚያስገነዝበን የንጉሡ ጠቅላላ ምኞት ፦

፩ኛ. ከክርስቲያኑ ከፖርቱጋል መንግሥት የጠበቀ የቃል ኪዳን ጓደኝነት አድርገው ዘወትር የሚያስጉዋቸውን እስላሞችን ለማጥቃት ።

፪ኛ. ከሠለጠነው የፖርቱጋል መንግሥት ዘንድ ልዩ ልዩ ጥበብ የሚያውቁ መምህራን አስመጥተው አገራቸውን ለማሠልጠን ነው ።

በየጊዜው በደዋሮ ፤ በአዳል ግዛት ከእስላሞቹ ባላባቶች ጋር ግጭቱ ባያቋርጥም እነሱንም ከሚደግፏቸው ከቱርኮች ፣ ከግብጾችም ጋር መፈራራትና መጠባበቅ ባይቀር እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከፊት ዠምሮ ንግሥት እሌኒም ዓፄ ልብነ ድንግልም ከእስላሞቹ መንግሥታት ጋር የጉርብትና ወዳጅነት እንዲጠበቅ ፈትነዋል ። ኢብን እያስ የሚባለው እንደጻፈው እ. አ. ቀ. በ፲፰፻፲፮ ዓ. ም. የኢትዮጵያ መላክተኞች ገጸ በረከት ይዘው ካይሮ ሄደው በዚህ ዘመን ለነበረው ለሱልጣን አልጋውሪ ያቀረቡትን እናስታውሳለን ። ስለዚህ ከነዚሁ አገሮች ጋር ንግድም ደብዳቤም መለዋወጥ ለጊዜው የተቋረጠ አይመስልም ። አሁን ደግሞ ቱርክ ግብፅንና አካባቢውን ከያዘ ወዲህ እስላሞቹ ባለፈው ለማጎቱዝ የሰጡት ወደፊት ደግሞ ለሚነሣው ለግራኝ አህመድ የሚሰጡት እርዳታ ለንጉሡ ለዓፄ ልብነ ድንግል ስለታወቃቸው በፊተኛው ጊዜ አውቀውም ሳያውቁም ችላ ሊሉት እስበው የነበረውን የፖርቱጋልን የወዳጅነት ግንኙነት በአሁኑ ጊዜ ለላ ማግረሚ መን

(1) Dernier partie du second Tome de l'Afrique-J. Temporal... ገጽ 253 - 256 ።

ገድ ስለሌለ አጥብቀው ፈልገውታል ማለት ነው ።
ከዚህ በፊት የፖርቱጋል የጦር መኰንኖች እነ ትሪስታን ደኩንሃ ፤ እነ ሎፔዝ
ሱአሬዝ በመርከብ እስከ ዘይላ እስከ ሞቃዲሾ እስከ ዛንዚባር ድረስ እየመጡ በእስ
ላሞቹ ወታደሮች ላይ የጦር ጉዳት ማድረጋቸውን አጠገባቸው ከአሉት ከነአልቫ
ሬዝ ፤ ከነቢርሙዴዝ ስለሰሙ ከእስላም መንግሥታት ጋር መስማማትም ለዘለቄታ
የማይቻል መሆኑን በመገመት የዚህኛውን የዝምድና ወይም የጉርብትና ግንኙነት
ለቀው በሃይማኖት ከሚቀርባቸው የባላጋሮቻቸው ባላጋራ ከሆነው ከፖርቱጋል
ጋር መሆንን እንደመረጡ ይታያል ። በደብዳቤያቸው ውስጥ ከእንግዲህ ወዲህ
ከግብጽም ከሌላም መልክተኛ አልቀበልም ሲሉ ጨርሰው መቁረጣቸውን ያስረ
ዳል ። ምናልባት ለጊዜው ይህ ዝኤባሉያቸው በእስላሞች ዘንድና በግብጽ እንዳይታ
ወቅ ፈልገው ይሆናል ። ነገር ግን ቁጥራቸው የበዙ መልክተኞች በሚመላለሱበት
ጊዜ ፤ አማኑኤል ሞቶ ኅዘኑን በአዋጅ ሲያከብሩ ፤ ከዚህ በፊት እንዳልነው ይኸ ቃል
ኪዳንና ዝምድና ለእስላሞቹ ሊሠወራቸው ዝምድናውም በማን ላይ መሆኑ ሊዘን
ጋቸው አይችልም ። ከሁሉ የበለጠ ደግሞ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን የእስላም ነክ
በሆኑት የጠረፍ አገሮች በምጥዋ ኤጺስ ቆጳስ ብለው ሲሾሙት ከዚህ በፊት እንዳ
መለከትነው በርሳቸው ዘንድ የብልሃት መንገድ ነው ፤ ቢሆንም ይኸን የመሰለው
ሁሉ የእስላሞቹን ጠብና ግንጋኔ እያባሰ ሊሔድ የሚችል ነው ።
ይሁን እንጂ ለአፄ ልብነ ድንግል የዚህን የፖርቱጋልን መንግሥት ቃል
ኪዳን ከመከታተል በቀር ሌላ ላገራቸው የሚጠቅም ነገር አለመኖሩን ስለተረዱት
ብቻቸውንም ሆነው የከበደውን የእስላሞች ወረራ እንደማይገፉት ስለተረዱ
እነሆ በደብዳቤያቸው ላይ ቃል ኪዳኑን አጥብቀው እንደጠየቁ አማኑኤልን በሽም
ግልናው እንደ አባት ልጁን ዮሐንስን በወጣትነቱ እንደ ወንድም አድርገው እርሳ
ቸው ወርቅና ብር ወታደርና ስንቅ እርዳታ ለፖርቱጋል ሰጥተው የሁለቱ ኃይል
ተባብሮ የእስላምን ኃይል እንዲሰብርና የአገራቸው ክርስቲያናዊ ሕዝብ በዕረፍት
እንዲኖር በወሰናቸው ላይ ተፋላሚ ባላባቶች እንዲደክሙ የጌታ መቃብር የሚገኝ
በት ኢየሩሳሌም ከቱርክ ገዥነት ነፃ ወጥቶ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ከዚያም
ወደዚህ መነኮሳቱና ምዕመናኑ እንደልባቸው እንዲመላለሱ ተመኝተዋል ። እንደ
ፈተኛው በዚህም ደብዳቤ ላይ ዮሐንስን አጥብቀው ሲጠይቁ የተመለከትነው ልዩ
ልዩ ጥበብ የሚያውቁ ፖርቱጊዞች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡና ሕዝባቸውን እንዲ
ያስለጥኑላቸው ነበር ። ከሁሉም አስቀድሞ ጠበንጃና መድፍ ሠራተኞች ይምጡ
ልኝ ያሉት የግራኝ ወራሪነት ቀደም ብሎ ስለተሰማቸው ባላጋራቸውን በመሣሪያ
እየተከላከሉ ለመቆየት ነው ። ዳሩ ግን ያለፈው ጊዜ በዋዛ ፈዛዛ ስላለፈ ያሁኑም
ጊዜ ስላጠረ በመሣሪያ እጦት ግራኝ እንደምን እንዳጠቃቸው ወደፊት እናነባለን ።
የሆነ ሆኖ ለዮሐንስ ፫ኛና ለሮማው ጳጳስ ለቀሌምንጦስ የሚሰጠውን ደብዳ
ቤና ገጸ በረከት ለፍራንቼስኮ አልቫሬጽና ለዶም ሮድሪግ ለአባ ጸጋ ዘአብ ሰጥተው
ከአሰናበቷቸውና እነሱም ባለፈው እንዳመለከትነው ፫ ዓመት መርከብ ሲጠባበቁ
በምጥዋና በአክሱም ቆይተው በ፲፭፻፳፮ ዓ.ም. በሚያዝያ ፳፰ ቀን እ.አው.ቀ. ከም

ጥዋ ከሔዱ በኋላ ያዔ ልብነ ድንግልን አስቸኳይ ጉዳይ በቶሎ ሔደው ሊያስፈጽ ሙላቸው አልቻሉም ። ከዚህ በፊት እንደተባለው የዚያን ዘመን ጉዞ ባሕሩ በመር ከብ የብሱ (መሬቱ) በከብትና በእግር ስለሆነ አንድ መላክተኛ ከኢትዮጵያ ወደ ሊስቦን ደርሶ እንዲመጣ ቢያንስ የ፯ ዓመት ጊዜ ያስፈልገዋል ። መላክተኞቹ ከሸዋ ወደ ምጥዋ ፤ ከምጥዋ ወደ ሕንድ (ጎአ) ከሕንድ ወደሊስቦን መሔድ አለባቸው ። በዚህ ላይ መርከብ መጠበቁ ፣ በየበሩ የቱርኮቹ ጥብቅ መቆጣጠር ፣ በነገሩ የሮማ ጳጳስ መግባት ደግሞ ከሊስቦን ወደ ሮማ መመላለስን ስለሚጠይቅ ይኸ ሁሉ ተጨ ማምሮ የጉዳዩን ፍጻሜ ወደኋላ ይጐትተዋል ።

በዚህ መካከል የሮማ ሊቀ ጳጳስንና የፖርቱጋልን ንጉሥ ከኢትዮጵያ የበለጠ በቅርብ የሚያሳስባቸው በቱርክና በፖርቱጋል ንጉሥ በፖርቱጋል ንጉሥና በሻ ርል ፭ኛ (የጀርመንና የኤስፓኝ ንጉሠ ነገሥት) መካከል በዙፋን መቀናቀን በግዛ ትና በበላይነት ምክንያት የሚነሣው ጠብና ክርክር ፣ ሉተር በዚህ ዘመን ያመጣው አዲስ የሃይማኖት የመሻሻል ክርክር ስለአለ ይኸ ሁሉ የኢትዮጵያን ጉዳይ አብዛ ኛ ጊዜ ችላ ስለአሰኘው መላክተኞቹ መልስ ሳያመጡ አሥር ዓመት አለፈ ።

አዔ ልብነ ድንግል ለጳጳሱና ለፖርቱጋል ንጉሥ ስለላኩት ደብዳቤዎች ጉዳይ የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ ለራሱ ዋና መላክተኛውንና ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገ ሥት የተጻፈለትን ደብዳቤ አሲዞ ከአልቫሬጽ ጋር ወደ ሮማ ሊቀ ጳጳስ ልኮ እነዚህ ሁለቱ መላክተኞች ከሮማ ጳ[illegible]ተገናኝተው በቁም ነገር ንግግር የተገናኘበትን እ.አው.ቀ.በ፲፭፻፴፫ ዓ.ም. ነው ። ይኸውም መላክተኞቹ ከኢትዮጵያ በ፲፮. በስ ባተኛው ዓመት ማለት ነው ። የንግግሩን ሁኔታና ለሮማ ጳጳስ የተጻፈውን ደብዳቤ ወደፊት እንመለከታለን ።

ስለዚህ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፖርቱጋልንና የኢትዮጵያን ሁለት የክርስቲያን መንግሥታት የወዳጅነት ግንኙነት ከየነጋዴውና ከተመላላሹ እየሰሙ ፣ ራሳቸ ውም እያዩ ይናደዱ የነበሩት የቱርክና የግብጽ ፣ የዓረብ አገር ባለሥልጣኖች መገና ሪያ ለማጎፉዝ ከአደረጉት የበለጠ በአዳልና በሱማሌ ለሚገኙት ባላባቶች የጦር መሣሪያና የወታደር እርዳታቸውን እያፋጠኑ በመስጠት ኢትዮጵያን ለማስወረርና የኢትዮጵያና የውጭ አገር የፈረንጅ መንግሥት የሚገናኝበትን በር በፍጹም ለመ ዝጋት ተነሡ ። ወደፊት በዝርዝር እንደምናነበው ዓረቦች ይህን አሳብ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ የሞከሩት ማጎፉዝ የሚባለውን ባላባት ይዘው ነበር ። ነገር ግን እርሱ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ተዋግቶ ከሞተ ወዲህ ከቱርኮችና ከዓረብ አገር ከዘቢድ ባሻ ከፍ ያለ የወታደርም የጦር መሣሪያም እርዳታ አግኝቶ ኢትዮጵያን ወርሮ የራሱንም የደጋፊዎቹንም የቱርኮችን ምኞት የፈጸመው የማጎፉዝ የልጅ ባል ግራኝ አህመድ ነው ። ለግራኝ አህመድ ደግሞ ወረራውን ያቃናለት ኢትዮጵ ያና ፖርቱጋል በወጠኑት ግንኙነት የተነሣ ከዓረቦች አገር ያገኘው የመሣሪያና የወታደር ድጋፍ ነው ። ስለዚህ አሁን የፖርቱጋሎችን ግንኙነት የመልክቱን ፍጻሜ ወደፊት በሥፍራው ስንደርስ እስከናነሣው ድረስ የግራኝ አህመድን እነሣ ሡንና በየጊዜው ያደረገውን ታላላቅ ጦርነቶች በዝርዝር እንመልከት ።

# ፫ኛ ክፍል
# የወረራው አጀማመርና አካሄድ

## ምዕራፍ ፳፮
## የ"ቦካን ጦር አውርድ" አለመታመን

የግራኝ አህመድ ትውልዱ ፣ አነሣሡና ወረራው በክርስቲያኖቹ ኢትዮጵያውያንና በእስላሞቹ በኩል ያለው አተራረክ ፈጽሞ የተለያየ ሆኖ ይገኛል ። ምንም እንኳን የጻፉት ወገኖቹ ቢሆኑም ታሪኩንም ቢያጋንኑለት ስለትውልዱና ስለአነሣሡ ከኛ ተረት ከሞላበት ታሪክ ይልቅ የእነርሱ አብዛኛው ጊዜ ያ.ረቅ ታሪክ የያዘው ጽሑፍ እንደሚታመን የምንገነዘበው የሁለቱንም ዓይነት አተራረክ ለመመልከት ወደ ጽሑፉ ስንገባ ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በ፲፭፻፰ ዓ. ም. በኤሚር ማኅፉዝና በሡልጣን መሐመድ ላይ የጦርነት ድል ካገኙ ዠምሮ ግራኝ እስከተነሣበት እስከ ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ድረስ አሥር ዓመት ያህል ዘመኑ የሰላምና የጸጥታ የተድላና የደስታም ጊዜ መሆኑ እርግጥ ነው ። በዚህ መካከል ከሁለት ዓመት በፊት በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. የደዋሮው ገዥ ነ፲፭፻፲፫ን ራሱ ፋኑኤል እስከ ሆባት ፋኑኤል አዳል ሄዶ መዋጋቱ አይዘነጋም ። ግራኝ ወደ ደዋሮ መጥቶ ፋኑኤልን አልወጋምና ድረስ ዘልቆ ግራኝን ወጋ እንጂ የግራኝ አጥቂነት የሚዠምረው ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ነው ።

ሰላም ሆኖ እርሻ ስለተስፋፋ ሰው ሁሉ በአፄ ልብነ ድንግል ጊዜ ዘመኑ ዘመነ በተድላና በደስታ በመኖሩ በዚያ ጊዜ የነበረውን ተድላ በማግነን ይልቁንም ግራኝ ስለመነሣቱና ዓፄ ልብነ ድንግልን ከነሠራዊታቸው ስለማጥፋቱ በቃለ አጋኖና በአንክሮ የተጻፈውን በቅርብ ጊዜ የታተመው ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የተጻፈው የዳግማዊ ምኒልክ ዜና መዋዕል እንኳን የአነጋገር መንገድ ይለውጥ እንጂ ይኸንኑ የቆየ ተረታዊ ታሪክ አጽድቆ ይተርካል (1) ።

በታሪክ ነገሥቱና በድርሳነ ራጉኤል ስለ ግራኝ አነሣሥ በግዕዝ የተጻፈው እንደዚህ የሚል ነው ።

«ለዓፄ ልብነ ድንግል ቦካን የሚባል ከተማ ነበራቸው ከዚያ ዘመኑ ዘመነ ሰላም ስለሆነ ቦካን ጦር አውርድ እያሉ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ጉግሥ በፈረስ እየተጫወቱ የገዛ ግንባቸውን በጦር ሲወጉ ግንቡ እየፈረሰ ምጽዋት የሚፈልጉትን ነዳያን አጠፉቸው ። ደግሞም እንደጋላ ሥርዓት የፈረሶቻቸውን ግንባር የቦረን ትቻ ደም እየቀቡ ትምባሆ እየጠጡ አምልኮ ባዕድን አድርገው ነበር ። በመጨረሻም ለጣና ቂርቆስ ጫን ዕጣን ፤ ለደብረ ሊባኖስ ጫን ዕጣን ስለት ሰደው አባቶቹ

(1) ምዕራፍ 7-9 .

ይኸን እያጠናችሁ ጦር አውርድለት ብላችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ ብለው ላኩ ።

በዚህ ጊዜ ቄስ አፄ ዮሐንስ ፡ ዓቃቤ ሰዓት ቃለ አዋዲ ፡ ጽራግ ማሠሬ ዘመለኮት የሚባሉት የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች መጥተው "እግዚአብሔር ጠላትን አጥፍቶ አገርን አስፍቶ ቢያስገዛዎ ጦር አውርድልኝ ብለው በየቤተ ክርስቲያኑ ጧፍ ዕጣን እየላኩ መሳልዎ ወዲያውም የክርስቲያን ንጉሥ ሆነው እንደጋላ የቦረንትቻ ደም የፈረስዎን ግንባር እየቀቡ ከአሽከሮችዎ ጋር በፈረስ ጉግሥ ሲጫወቱ የገዛ ግንብዎን በጦር እየወጉ ግንቡ እየተናደ ምጽዋት የሚፈልጉትን ነዳያን ማጥፋቱ ፤ ትምባሆ መጠጣትዎ ይህ ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያጣላዎ ነው" ብለው በወዳጅነት ቢመክሯቸው «ገፋዒ ነዳያን አደረጋችሁኝ - ይሀ በዳይ አደረጋችሁኝ» ብለው በቁጣ ቃል ወደ ድንኳናቸው ገብተው ግብር ሳያገቡ አደሩ ።

በበነጋው ክርስቶስ በሰውነቱ የጸጋ ልጅ ነው የሚል አንድ ኢትዮጵያዊ ተነስቶ ተዋሕዶዎችን ከንጉሡ ጋር ያጣላ መስሎት ትምባሆ አትጠጡ የሚል መጽሐፍ ወዴት አለ ? ወንጌል ወደ አፍ የገባ ሁሉ ሰውን አያረክሰውም የሚያረክሰው ከአፍ የወጣ ነው ይላል ብሎ ክርክር ቢያነሳ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ከአፍ የወጣ የተባለው አምልኮ ባዕድና ገቢረ ሥራይ አይደለምን ብለው ቢመልሱለት ሮማውያን አሉና ሮማውያን በፍርድ አያብሉም በፍርድ ያስረታኛል ብለው ክርክሩ ሳይፈጸምና በአደባባይ ሳይ[illegible] ንጉሡ ተነሥተው ወደ ግቢያቸው ገቡ ። መነኮሳቱም ምክራችንን ካልተቀበሉን ንጉሡ ራሳቸውን ይጐዳሉ እንጂ እኛ ምን ቸገረን ብለው እያዘኑ ወደ ደብረ ሊባኖስ ተመለሱ ። አክዓብና ኤልዛቤል ሚስቱ ነቢያተ እግዚአብሔርን ስላስገደሉ ኤልያስ ሰማይና ምድርን ዘግቶ ፫ ዓመት ከመንፈቅ ረኃብ እንደጸና በአፄ ልብነ ድንግል የመነኮሳቱን ምክር አለመስማት እግዚአብሔር ስለአዘነ አህመድ ግራኝን አስነሣባቸው ። አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ ፡ መጻሕፍት ተቀነጸጸሉ ፤ ምዕመናን እንደበግ ታረዱ ፡ ደማቸው እንደ ውኃ ፈሰሰ ፡ አጥንታቸው ተከሰከሰ ።

ዓፄ ልብነ ድንግልም በሠሩት ጥፋት ግራኝን እንዳሥነሳባቸው ስላወቁ እየተዋጉ ሲሸሹ ሱባዔ ገብተው የሠራሁትን ኃጢአት ይቅር በለኝ እያሉ አልቅሰው እዝነው እግዚአብሔርን ለመኑ ፤ እግዝእትነ ማርያምንም ከልጅሽ አማልጅኝ ብለው ቢለምኗት ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ራጉኤልን መልአከ ብርሃናትን ቅዱስ ጊዮርጊስን ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አስከትላ መጥታ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል እስከመጨረሻው ተናገረቻቸው ። ቃሉም ይህ ነው ፡ «እኔን ሳትወደኝ ለምን ስሜን በምስጋና ታነሣለህ ፡ አሁንም ጸሎትህን አልሰማም ያባትህን የወዳጁን የናዖድን ትእዛዝ አፍርሰሃልና ልጄ በዳዊት አፍ አድሮ የኃጢአተኞችን ጸሎት አልቀበልም ብሎ የተናገረውን አልሰማህምን» ብትላቸው መልሰው «የእኔን ኃጢአት ሳትዘክሪ ያባቶቼን የዘርዓ ያዕቆብንና የናዖድን ነገር አስበሽ ከልጅሽ ከወዳጅሽ አስምሪኝ» አሏት ። ያን ጊዜ ምሕረት ልማድዋ ስለሆነ «እንግዲህ በነፍስህ ደስ ይልሃል በሥጋህ ታዝናለህ በስደት ትሞታለህ አሁንም ንስሐ ግባ ከናዖድ ዘር መንግሥት እንዳ

ይጠፋ አድርጓልና የልጅ ልጆችህም እንደ ናዖድ የእኔን ኪዳን ጠብቀው ቢኖሩ መንግሥታቸው ይጸናል ። ባይጠብቁ ግን መንግሥታቸው ትጠፋለች አገራቸውም ለአሕዛብ ትሆናለች» አለቻቸው ። አፄ ልብነ ድንግልም «የምሞትበት አገር ወዴት ነው ልጆቼስ ከወዴት ነው የሚነሡት» ቢሏት ፤ «ከእንግዲህ ወዲህ መል አኩ ራጉኤል ይነግርሃል ብላ ከዓይናቸው ተሰወረች» ይላል (1) ።

ስለዚህ መላእክት ከእግዚአብሔር ወደነቢያት እየተላኩ ይነግሯቸው እንደ ነበረ እንደዚሁም መልአኩ ራጉኤል በራዕይ ተገልጾ «አንተ በስደት ትሞታለህ ፤ ከልጆችህም ውስጥ ገ ፣ ይነግሥ (ገላውዴዎስ ይነግሣል) ፤ ፊ ፣ ይመውት (ፊቅጦር ይሞታል) ፤ ሚ ፤ ይሠየጥ (ሚናስ ይሸጣል) ፤ ያ ፤ ይነብር (ያዕቆብ ይኖራል) እያለ ወደፊት በራሳቸውና በልጆቻቸው የሚደርሰውን ጨርሶ ነግሮአቸዋል» ይላል ። ይህ ሁሉ በየታሪክ ነገሥታችን በተለይም በድርሳነ ራጉኤል ተጽፎ እስከዛሬ ይነበ ባል ።

ስለዚህ ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ምክንያት እግዚአብሔር አህመድ ግራኝን አስነሳባቸው ለማለት ነው ። ይኸንንም የኛን የጽሑፍ መሠረት በማድረግ የውጭ አገር ደራሲዎች እነሞሪዬ ሳይቀሩ በመጽሐፋቸው ጠቅሰውታል ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ «ቦካን ጦር አውርድ» እያሉ ይሳሉ ነበር ። ጭንት ዕጣን ለጣና ቂርቆስና ለደብረ ሊባኖስ ገዳማት እየላኩ ይኸን እያጠናችሁ ጦር አውርድለት ብላችሁ ለምኑልኝ ይሉ ነበር የሚለው ይነበባል ። እንደ እውነቱ ከብዙ ዘመን ዝምሮ ተጽፎ የቆየ ስለሆነ ሲባል የቆየውን ሳያወሱ በዝምታ ውስጥ ማለፍ ሳያስተባብሉም ጉዳዩን ወደጐን አድርጎ መዝለል እንደማመን እንዳይቆ ጠር ወይም አንባቢን ከጥርጣሬ ውስጥ ለማስወጣት አለመሞከር አግባብ ስላልሆነ ይጠቀሳል እንጂ እንኳን ታሪኩ ለመታመን በዛሬ ጊዜ ቁም ነገር ባለበት ጽሑፍ ጐን ሠፍሮ መገኘቱና መነበቡ ቅር ያሰኛል ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ከአዲስ አበባ ደቡብ ምሥራቅ የረር አጠገብ ዛሬም የሕ ንፃ ምልክቱ የሚታየው ቦካን የሚባል ከተማ እንደነበራቸው የታወቀ ሲሆን በዚህ ከተማ ሲኖሩ መንግሥታቸው የተድላና የደስታ ዘመን ቢሆን በዚሁ ተደስ ተው ይኸንኑ ላደረገላቸው አምላክ ምሥጋና በመስጠት ፈንታ እንደዚህ የመሰለ የዕብሪትና የልጅነት ሥራ አደረጉ ብሎ የቀድሞን እንጂ የዛሬን አንባቢ ማሳመን ያስቸግራል ። በ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. ከተደረገው ከማኅፋዝ ጦርነት ወዲህ የተገኘው ሰላም አሥር ዓመት አይሞላም ። ለዚያውም ቢሆን የአዳልና የሱማሌ አገሮች በዘ መናቸው እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያሉት ጸጥ ለጥ ብለው ሳይገዙ አልፎ አልፎ ግጭት ማድረጋቸው የታወቀ ነው ።

ከዚህ በፊት እንዳልነው በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. የደዋሮው ገራዶቸው ፋኑኤል ከግ ራኝ ጋር የመገዣመሪያውን ጦርነት ማድረጉን ወደፊት እናነባለን ።

(1) "እንከስ ይንግርከ ራጉኤል መልአክ ብርሃን ዘሀሎ ምስሌየ ወዘንተ ብሂላ ተሠወረት እምአዕይን ቲሁ" የኢት ዓመታዊ መጽሔት ቊ 2 ገጽ 96 - 100

ለዚያውስ ቢሆን በሰላም ፈንታ ጦርነትን በስለት ከሚፈልጉ "ቦካን ጦር አውርድ" እያሉ መሬት ከሚደበድቡ ወደ ሰሜን ዘምተው ግብፅን ለመያዝ ከቱርክ ቢዋጉ ይኸም የሚበዛባቸው ቢሆን የራሳቸውን የኢትዮጵያ ወደቦችና ደሴቶች ምጥዋን ዳህላቅን ከቱርክ ፥ ዘይላንና ዙላን ከዓረቦችና ከወላስሞች ለማስለቀቅ ቢፈልጉ የሚዋጋቸው ይጠፋ ኖሮአልን ።

ስለዚህ ለድሉ ተሳሉ ቢባል ያምራል እንጂ ጦርነት በማጣት ተቸግረው ለየገዳማቱ ጧፍ ዕጣን እየላኩ ይሳሉ ነበር ማለት በፍጹም የማይመስል የተራ ወይም የየዋህ ሰው አጻጻፍ ነው ። ይኸንንም አጻጻፍ በዛሬ ጊዜ ለማመን የሚፈልግ እንደዚያው እንደጻሐፊው በአስተያየት ገና ወደ ኋላ የዘገየ ገራገር አንባቢ መሆን ነው ።

በታላላቆቹ የክርስቲያን ነገሥታት አባቶቻቸው በነአጼ ዘርዓ ያዕቆብ በነአጼ ናዖድ ቤተ መንግሥት በሥርዓትና በመንፈሳዊ አስተዳደግ ያደጉት አጼ ልብነ ድንግል ጦር አውርድ ብለው ባይሳሉ የገዛ ግንባቸውን በጦር ባይወጉ ድሆችን ባይበድሉ ትምባሆ ባይጠጡ ኖሮ ይኸ ሁሉ የጦርነት መከራ በዘመናቸው አይደርስባቸውም ነበር ተብሎ በመላ የተለጠፉባቸውን የታሪክ ገጽ ለዘለቄታ ከአሳብም ከጽሑፉም ገጽ ላይ መሠረዝ ተገቢ ነው ።

ግራኝ አህመድ ለጦርነት ከመነሣቱ በፊት በዋዜማው በነበሩበት ስድስት ዓመታት ውስጥ ጧትና ማታ እየተገናኙ በቅርቡ እያነጋገሩ ያወቋቸው የፖርቱጋሉ ተወላጅ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በጻፉው መጽሐፍ ላይ እንደተገነዘብነው ሰውዬው እንዲያውም ከሥጋዊነትና ከወታደርነት ይልቅ መንፈሳዊነት የሚያጠቃቸው ሆነው ይታያሉ ። በዚሁ መጽሐፍ ላይ «ንጉሡ ነገሥቱ መልካምና ቅዱስ ነው» ብለው በኢትዮጵያ ከሃምሳ ዓመት በላይ የተቀመጡት ከርሳቸው ጋር ዘመናቸውን የፈጁት ግብፃዊው ጳጳስ አባ ማርቆስ ለፖርቱጋሉ አምባሳደር ለሮድሪግ ደ ሊማ እንዳሜወቱት ያነበብነው ትዝ ይለናል ። ጳጳሱ ለእንግዳው አምባሳደር ይኸን አስተያየት የሰጡት ግራኝ ከመነሣቱ ሦስት ዓመታት ያህል ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ።

በግራኝ ጦርነት ዋዜማ በድልወትና በዕረፍት ፈንታ የነበረባቸውን ችግር ለፖርቱጋል ነገሥታት ላባትዬው ለአማኑኤልና ለልጁ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ያስረዳሉ ።

በነዚህ ደብዳቤዎች ላይ የጦርነቱ ስለት ጉዳይ ወደጉን ይሁንና ይልቅስ በላያቸው ላይ ከብዶ የመጣውን የጦርነት ደመና በምን አኳኋን ሊመልሱት እንደሚችሉ የነበራቸውን ሥጋት ለዚሁም ፩ ረዳት የክርስቲያን መንግሥት አጥብቀው እንደሚፈልጉ በትክክል ይገልጻሉ ። "ጦር አውርድ" ብለው መሬት ስለ ደበደቡ ግንባቸውን እየወጉ የፈረሰው ግንብ ነዳያንን ስለመታ ትምባሆ ስለጠጡ ግራኝን አስነሳባቸው ብለው የጻፉባቸው ካህናት ወይም ምዕመናን በቱርክና በፖርቱጋል መካከል ያለውን የዘመኑን የግዛትና የጥቅም ሽሚያ በኢትዮጵያና በደቡብ እስላሞች በወላስሞቹም መካከል ያለውን የቆየ የጠብ ውዝግብና የበቀል ፍላጎት የግራኝንም የጋለ የገዥነት ፍላጎትና ያመራር ዘዴውን በጀርባው የተደገፈውን የዕር

ዳታ መጠን በጠቅላላው የዘመኑን ሁኔታ ለማመዛዘን ያልቻሉ መሆናቸው ጥርጥር የለውም ።

መቸም አፄ ልብነ ድንግል እንደ ጳጳሱ አነጋገር ፍጹም ጻድቅ ሳይሆኑ እንደ ማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር ኃጢአትም በጎ ተግባርም የተዋሐዳቸው ተቀብተው እንደመንገሣቸው መጠንም በንጉሣዊ ኩራት ባለፈና በኖረ ወግና ሥርዓት የተጠ መዱ ባላቸው የጦር ሠራዊትና የአለቆች ብዛት የሚመኩ ሊሆኑ ይችላሉ ። ከዚህ በፊት የጠቀስነውን ዝግጅት ከማድረግ በቸልታና ጠላትን በመናቅ የቦዘኑ ፤ በፍ ጹም ክርስቲያንነታቸውም ላይ በጸሎቱና በጾሙ በትሩፋቱም መካከል ምናልባት በዙሪያቸው የከበባቸው ሕዝብ እምልኮ ባዕድ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ገብቶ እን ደማናቸውም ነገሥታት እርሳቸውንም አልፎ አልፎ ሳያውቁ በስሕተት አውቀ ውም በድፍረት ገጥሟቸው ይሆናል ። የሕይወታቸው ዝርዝር ታሪክ ስለሌለ ከዚህ የበለጠ የኝህን ንጉሥ የጠባያቸውንና ያመራራቸውን ሁኔታ ለማብራራት ችግር ነው ። ከዚህ በላይ የሰጠነውም መግለጫ ሳይበቃ አይቀርም ፤ ከመብቃትም በዝቶ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ወደፊት ባሉት ምዕራፎች እንደምናነበው ከዚህ በፊትም እንዳነበ ብነው የግራኝ አህመድ አነሣስ በሰውዩው በራሱ ከፍ ያለ የገዥነት ምኞትና እንደ ዚሁም በአመራር ዘዴው ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከተከታዮቹ ነገዶች በቀልፍለጋ ጋር የታወቀውን የቱርኮችን ወረራ በርሱ ውስጥ ያሉትን የዘቢድና የየመን ዓረቦችን መስፋፋት የተደገፈ ነው ። የዚህም የቱርክ የወረራ አደጋ ያፄ ልብነ ድንግልን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ባለፈው እንዳነበብነው ግብጽንም ከዚያ ግሪክንም ዓረብ ንም መላውን የባልካን አገሮች ቡልጋሪያን ፤ ዩጎስላቪያን ፤ ሩማንያን ፤ አርመንን ፤ የነምሳን አጋማሽ ሳይቀር ይነስ ይብዛ በዚሁ ዘመን አልማራቸውም ። ወረራውም የደረሰው ተወራሪው እየተሳለ ሳይሆን በግድ ዘመን በወለደው ኃይለኛ ፊት እየተ ሸነፈ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ISIC

ኢትዮጵያን ግን የቱርክ ቀጥተኛ ወረራ ሳይደርስባት በሩቁ በርሱና በቅርቡ ከቀይ ባሕር ማዶ ባሉት ዓረቦች የተደገፈውና ከአገር ውስጥ የተነሣው ግራኝ አህ መድ ሊያሸንፋት ቻለ ። መሸነፍም የመጣው ዝርዝር ምክንያቱን ወደፊት ባለው ምዕራፍ እንደምንገልጸው ዋናው የግራኝ ረዳቶች የኢትዮጵያ ጐረቤቶች ሲሆኑ ለኢትዮጵያ ረዳት ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የፖርቱጋል መንግሥት ግን በአውሮፓ ሩቅ በመሆኑ ነው ። በዚያን ዘመን የፖርቱጋል የቅኝ ግዛት የነበረው ሕንድ (ጐአ) የኢትዮጵያ ወሰንተኛ ቢሆን ኖሮ የግራኝ ወረራ በቀላሉ ሊከናወን ባልቻለ ። ወረራው በተፈጸመ በ፲፩ኛው ዓመት የደረሰው የፖርቱጋሎቹም ርዳታ በጦርነቱ መገመሪያ ላይ በሺ፭፻፲፱ ዓ. ም. ሊደርስ በቻለ ነበር ።

ስለዚህ መደምደሚያውን ግራኝ አህመድ በኢትዮጵያ ላይ የተነሣው በራሱ የገዥነት ምኞት ባለፈው የክርስቲያኖቹ ነገሥታት ሳያቋርጡ ወላስሞቹ በሸፈቱ ቍጥር ድል እያደረጉ የፈጸሙትን ዘረፋና ደም ማፍሰስ ለመበቀል በተለይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ወዳጅነት ስለወጠኑ ከሩቁ ከቱርኮቹና

ከዓረቦቹ ተገፋፍቶ እንጂ አባቱ በደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ተደብድቦ በመሞቱ ወይም በተድላ በደስታ ምክንያት ከልክ ያለፈ ደልቷቸው "በነገ ጦር እውርድ" ብለው በመሳል አይደለም ። እላይ እንዳመለከትነው ዘመናቸውም ሙሉ የሰላም ዘመን አልነበረም ። በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ከማኅፉዝ ከተዋጉ ወዲህ እንኳ እልቫሬዝ በነበሩ በት ጊዜ በ፲፭፻፲፪ - ፲፯ ዓ. ም. ላይ አንዱን ቢትወደድ በጥፋት ንጉሡ ቢያሥሩት የአዳሉ ንጉሥ አስፈትቶ ወሰደው ማለትን እንደሰሙ ደግሞ ሌላው ቢትወደድ ሊዋጋ ወደ አዳል መዝመቱን ዓይተዋል (1) ።

በተረፈ ከዚህ ሁሉ ጋር የኢትዮጵያና የፖርቱጋል ወዳጅነት ለጦርነቱ ዋና መንሥኤ ከሆኑት ምክንያቶች ዋነኛው መሆኑ አይጠረጠርም ። ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ከተነሡትና ከጉዞ ላይ ካሉት ከ፫፻፵፰ ክርስቲያኖች ፲፰ቱ ብቻ ሲተርፉ የቀሩትን ሱዋኪንን እንዳለፉ እስላሞቹ ፈጅተዋቸው እንደነበረ ከተረፉት ውስጥ ግማሾቹን አልቫሬዝ ምጥዋ ላይ አግኝቷቸው "ይኸ ሁሉ ጥቃት የደረሰብን በና ንተ ወዳጅነት ምክንያት ነው" ብለው እያማረሩ እንደነገሩት ጽፏታል (2) ።

በተለይ ደግሞ(La Croze)የሚባለው በ፲፯፻፴፱ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፉ ላይ እንደዚህ ይላል "ንጉሡ ዳዊት (ልብነ ድንግል) ሮድሪግ ደ ሊማን በደስታ ተቀ በለው ። በርሱም አማካይነት አንድ የማጥቂያና የመከላከያ ስምምነት ከፖርቱጋል ንጉሥ ጋር መሠረተ ። ይኸም ስምምነት ቱርኮቹንና እስላሞቹን ከቀይ ባሕር ዙሪያ ከያዙት አገር በሙሉ [illegible]ረር ነበር ። ይኸን የመሰለው ስምምነት ለብዙ ጊዜ ምሥጢር ሆኖ ሊቆይ አልቻለም ። የእስላሞቹ መሳፍንት በተለይ ንጉሡ ነገ ሥቱ ለሚገዛቸው አገሮች ጐረቤት የሆነው የአዳል ንጉሥ በጉዳዩ ተሸበሩ ። ስለ ዚህ የአዳሉ ንጉሥ የኢትዮጵያንና የፖርቱጋልን ግንኙነት ለማጥፋት ሰላይ አበ ጅቶ ጦርም ሰብስቦ አንድ ጐበዝ የጦር ሹም (ካፒቴን) ኢትዮጵያን ድል አድርጎ ለመያዝ ይፈትን ዘንድ ላከ ። ይኸም የጦር አለቃ አህመድ የተባለውና በመጠሪያ ስሙ ላይ በተጨማሪ ተሠይሞ ግራኝ የተባለው ነው (3) ።

## ምዕራፍ ፳፰

## ስለ ግራኝ አህመድ ትውልድና አነሣስ - ከፋኑኤል ጋር ያደረገው የመዠመሪያው ጦርነት (፲፭፻፲፯ ዓ. ም.) ።

ያለፈው ምዕራፍ ጦርነቱ የተነሣበትን ምክንያት በኢትዮጵያ ጽሑፍ በኩል ያለ ውን ያገራችንን የቆየውን ተረታዊ ታሪክ አመልክቶናል ። ያሁኑ ደግሞ ስለግራኝ አህመድ ልደትና ዕድገት በኛ ዘንድ በሁሉም ጽሑፍ ላይ ሳይሆን ባንዳንድ ክፍል

(1) አልቫሬዝ . . . . . ገጽ 320
(2) " ምዕ. 129 ገጽ 335 - 336
(3) Histoire du christianisme d'Ethiopie et d'Armenie N.Maturin Veyessiere La CROZE ገጽ 86 - 87

የተጻፈው እንደዚያው እንዳለፈው ልብ ወለድ ታሪክ ነው ። ያገራችን ታሪካዊ ሥነ ጽሑፍ ተበታትኖ በያለበት የሚገኘው ሁሉ አንዱ በአጭሩም ቢሆን ሐቁን ታሪክ ሲከተል ሌላው ረዘም አድርጎ ከሐቅ ውጭ የሆነ የተረት አነጋገር አስፍሮ ይተርካል ። ነገሩን ከሥሩ ያልመረመረ ግራና ቀኝ ስለዚያው ጉዳይ በየመልኩ ፡ በየቋንቋው የተጻፈውን ያላስተዋለ አሳቡን ወደኋላ መልሶ በዘመኑ ላይ ያለውን የፖለቲካና የጦርነት ውዝግብ ያልተረዳ እንግዳ ደራሽ አንባቢ ሐቀኛውን ታሪክ ከተረቱ ለይቶ ለማወቅ ይቸገራል ።

መቼም ሥነ ጽሑፋችን ባለፉት ምዕራፎች እንዳመለከትነው የተደረሰው በቤተ ክህነት አባቶች በመንፈሳዊ አስተያየት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከገድልና ከድርሳን ጋር ተሰባጥሮ የተጻፈውን ሁሉ ለዘመኑ የአንባቢ አእምሮ ለዘመኑ የትምህርት አሰጣጥ እንደሚመጥን አድርጎ በየቅርንጫፉ ያለውን አበጥሮ ለማቅረብ ገና ብዙ ጊዜ ይወስዳል ። ይኸው የተያዘው ዘመናዊ ትምህርት በየሰዉ አእምሮ ሥር በሰደደ መጠን እስካሁን ሲታመን ቢቆይም የተረቱ ሥነ ጽሑፍ ሥሪቱን እየለቀቀ እንደሚሄድ የታወቀ ነው ። ጊዜም ባደረገበት ጉዞ ሁሉ የሥነ ጽሑፍን የእምነትን መልክ ብቻ ሳይሆን የቅርጽን ፤ የሥዕልን ፤ ያስተዳደርን የሌላውንም መልክ ሁሉ በየጊዜው እየለዋወጠ መጥቶ እስከዚህ ደርሷል ። ይኸም ያሁኑ የሥነ ጽሑፋችን መልክ የመጨረሻው ሳይሆን ወደፊት በሚተካው ትውልድ ዘንድ ሌላ አስተያየትና አስተሳሰብ እንደሚወለድ የታወቀ[ISIC] ።

አሁንም ስለግራኝ ልደትና ዕድገት ለመተረክ ሲሞከር ያገራችን አንዱ ክፍል ታሪክ እንደዚያው እንደቦካን ጦር አውርድ በማመሳሰል እንደዚህ እያለ ይተርካል ። «የአዳል ባላባት ፺፱ ነጭ በቅሎ ፤ ፶ የወርቅ ቡችላ ፤ ፴ ኩሉ ምንጣፍ ፤ ፻፱ ሻማ ፤ ፪ሺ ፍሪዳ ፤ ፫ሺ የፍየልና የበግ ሙክት ለአፄ ልብነ ድንግል በየዓመቱ ይገብር ነበር ። እንደዚሁም የግራኝ እናት ሺምሺያ (ፀሐይቱ) የሐረር እስላም ነበረች ፤ እርሷም በበኩሏ ግብር ይዛ ወደ ደብረ ሊባኖስ ወረደች ፤ በዚያም አንድ መነኵሴ ተገናኝቷት ፤ ሴቲቱ ግን ወደ ሐረር ተመልሳ ግራኝን ወለደች ። ግራኝም ካደገ በኋላ ጓደኞቹ በጨዋታም በምርም "አንድ ጉን" ይኸውም ማለት እናት እንጂ አባት የሌለው እያሉ ዘወትር ይሰድቡት ነበርና እናቱን አባቴን ንገሪኝ እያለ ነዘነዛት ፤ እርሷም አባቱ የደብረ ሊባኖስ መነኵሴ መሆኑንና እርሱንም የደብረ ሊባኖስ ቀሳውስት ደብድበው እንደገደሉት አስረዳችው ። ከዚያ በኋላ ያባቱን ደም ለመበቀል ኢትዮጵያን ወረረ ፤ የደብረ ሊባኖስን ገዳምና ሌሎችንም አብያተ ክርስቲያናት አቃጠለ መነኮሳቱንና ቀሳውስቱንም ፈጀ ።»

ይኸም ታሪክ በግማሹ እውነት ቢኖር እያለፈ ጣልቃ እያገባ የሚተርከው መሠረት የሌለው አፈ ታሪክ ከመሆን አይዘልም ። እውነት ነው ብለን የምናምነው ከኡመር ወላስማ ዘር የወረደው የይፋቱም ይሁን የአዳሉ ባላባት ሲመቸው እየሸ

ፈተ ሳይመቸው እየገበረ መኖሩ የታወቀ ነው ። የግብሩ መጠን ፯፻ ነጭ በቅሎ ፣ ፻ የወርቅ ቡችላ ያለው ይኸን ያህል ሃምሳ ቡችላ የሚመዝን የበዛ ወርቅና ቀለሙ አንድ ዓይነት ያውም ነጭ በቅሎ ያውም በያመቱ እየተገኘ መገበሩ አጠራጣሪ ነው ። ከመነኮሴ መወለዱ ይቅር እንጂ ግራኝ ወረራው በያለበት ከቀናው በኋላ ደብረ ሊባኖስን እንደቀሩት ገዳማት ማቃጠሉ የታወቀ ነው ። ነገሩን ሲመለከቱት ይኸ ባይሆን ኖሮ በቤተ ክርስቲያንና በቀሳውስት ላይ ያን ያህል አያጨክነንም ነበር ተብሎ በመላ የተፈጠረ መሆን አለበት ። ከእስላሚ ውድቀት ያገኘው መነኮሴስ ሆኖስ ቢሆን ባይሆን ከቤተ ክርስቲያን ተወግዞ መወገድ እንሶት እንደ አባብ እንዴት ተቀጥቅጦ ይሞታል ? ። ሁኔታውስ ከወንጌል ትእዛዝ ውጭ አይሆንምን ?

ይኸ አተራረክ ግራኝ አህመድ ቁመናው ከመጠን ያለፈ ጉራዴው አርባ ክንድ ጦሩም አርባ ክንድ ነበር ፣ ትልቅ የደንጊያ ቋጥኝ በቀላሉ ይወረውራል ከሚባለው ከሕዝባዊ የተረት አነጋገር ጋር የተመሳሰለ ነው ። ጉንደር ከተማ አቅራቢያ በእምፍራዝ ውስጥ ሰንደባ ኢየሱስ (ደብረ ሐሊም) የሚባል የሚያስደንቅ በጥርብ ደንጊያ የተሠራ መቅደስ አለ ። በዚህ ዓመት ለጉብኝት በሄድሁበት ጊዜ በቤተመቅደሱ ውጭ ፲ ሜትር ቁመት ያለው ወፍራም ደንጊያ ተጋድሞ የሚታየውን መምህሩ ግራኝ በሩቁ ወርውሮ ቤተ ክርስቲያኑን የመታበት ነው ሲሉ በቱም ነገር የተናገሩት ትዝ ይለኛል ። እንደዚሁም በሸዋም በብዙ ጠረዳ ከፍ ያለ ደንጊያ ግራኝ የወረወረው ወይም ፈረሱን ያሠረበት ነው ከሚባለው ጋር የተመሳሰለ ነው ።

የግራኝ አህመድ እውነተኛው ታሪኩ በፈረንጆችም በዓረቦችም በወገኖቹ በሱማሌዎችና በሐረርጌዎችም ዘንድ ያው የተቻለው ያኸል የታወቀ ነው ። ባገራችንም ያሳጥር እንጂ ባጭሩ አድርጎ ስለ ግራኝ የሚናገረው ታሪክ ነገሥታችን ለብቻው በሐቅ መንገድ ጽፎት ይገኛል ። ይኸው እውነተኛ ታሪክ ነገሥት ግራኝ የደብረ ሊባኖስ መነኮሴ ልጅ አለመሆኑን ሲያስረዳ « . . . . . ባዒ ልብነ ድንግል ላይ በኢብራሂም ልጅ በአህመድ እጅ የመጣው ጥፋት» ብሏል (1) ።

ከሁሉም ይበልጥ ስለግራኝ አህመድ ስለልደቱና ዕድገቱ ስለ እንግሥና ስለ ወረራው ፈረንጅም ዓረብም መሠረት ያደረገው "ፍቱሕ አል ሐበሽ - የሐበሻ ወራዎች" በሚል አርዕስት ሺሃብ ኤዲን አሕመድ ቤን አብደል ቃድር (ዓረብ ፋቂህ) የሚባለው የዓረብ ተወላጅ የጻፈውን ነው ። እርሱም ግራኝ በዋለበት እየዋለ ባደረበት እያደረ ጦርነቱንም እየተከታተለ ባይኑ ካየውና አቡበከር ከሚባለው እንደ በት እየሰማ በቀረው የጦር ግንባርም ራሱ እየተገኘ ወይም ከተማረኩ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ እየሰማ የጻፈው ነው ። ስለኢትዮጵያ ታሪክ ጉዳይ በብዙ የደከሙት ታሪክ ነገሥታችንን ወደ ፈረንሣይኛ ማስታወሻ እየጨመሩ የተረጐሙት ሙሴ ሬኔ ባሴት አሁንም ይኸንኑ ስለግራኝ ጦርነት መደበኛ ታሪክ የያዘውን ያረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ፈረንሣይኛ ከራሳቸው ብዙ ምስክር በየምዕራፉ

(1) ወህየንተ መንሱት ዘመጽአ ላዕሌሁ በእደ አህመድ ወልደ ኢብራሂም . . . . ታሪክ ነገሥት ገጽ ፰

ISIC

# [f° 1] بسم الله الرحمان الرحيم

الحمد لله المنان[1] ، ذي الفضل والجود والاحسان ، الذي جاد بالعطاء قبل السؤال واسبغ علينا النعم[2] والافضا والامتنان ، وبدأ بالايجاد واردفه بالامداد وتابع النوال فلله الحمد على عطائه الجزيل المنان[3] ، وفضله الذي لا ينقطع ولا ينحصر بعد ولا ميزان ، واشهد ان لا اله الا الله وحده لا شريك له واشهد ان سيدنا محمدا عبده ورسوله ، ارسله الينا رسولا امينا مبينا نبيا[4] نبي الاميين محمد[ا] المصطفى والنبي المجتبى[5] صلى الله عليه وسلم ما اختلف الملوان ، وعلى اله واصحابه الذين[6] نصروا الدين القويم بالسيف والسنان ، وبذلوا الاموال والمهج وفارقوا الاهل والاوطان ، .......

.................................

— ٣٤٧ — ISIC

كلهم اشراف مع شيخهم شرف الدين بن علي ، والشريف محمود ، والشريف عبد الرحمان ، وتقبلهم الامام ، واعطاهم ارض اطراف بلدان[1] الى طرف النوبة ، واصطلحت جميع الدنيا الى بلاد النوبة ، والحمد لله على دين الاسلام الذي اظهره الله على جميع الاديان ، وجعل المجاهدين المخلصين احد الاركان ، وصلى الله وسلم[2] على سيدنا محمد المختار من ولد عدنان وعلى آله واصحابه ما اختلف الملوان ، وعلى التابعين لهم وتابعيهم باحسان[3] ، والحمد لله رب العالمين ، حمدا كثيرا طيبا مباركا كما يجب ، ربنا تعالى ويرضى[5]

............

የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን የአረብ ፋቲሀን መጽሐፍ ያረብኛውን ታሪካዊ ጽሑፍ የሚያሳየው ።

ግርኜ እየጨመሩ ተርጉመውታል ።

ይሆን መጽሐፍ የጻፈው ሺሃብ ኤዲን አህመድ አብድል ቃድር ባሜሩ ይግሞ ዓረብ ፋቂህ ተብሎ የተሰየመው በየመን ውስጥ የጂዛን ተወላጅ ነው (1) ። በሸምብራ ኩሬ ግራኝ አህመድና ዓፄ ልብነ ድንግል ተዋግተው ንጉሡ የተሸነፉ ዕለት በጦርነቱ ላይ ነበር ። ዘሩ ዓረብ ሃይማኖቱ እስላም ተከትሎ የመጣው ግራኝ አህመድን ስለሆነ በአጻጻፉ ላይ የክርስቲያኖቹን ወገን የማኩሰስ የእስላሞቹን ወገን የማጋነንና የማድነቅ አጻጻፍ በብዙ ይታይበታል ። ለምሳሌ በየምዕራፉ አንድ እስላምና አንድ ክርስቲያን የተዋጉትን ከሚተርክበት ላይ «እገሌ እስላሙ ገነትን ያውርሰውና በእገሌ በክርስቲያኑ እጅ ሞተ እርሱንም (ክርስተያኑን) ለገሀነም ያዳርገው» ማለት ልማዱ ነው ።

ይኸም በእርሱ ላይ ብቻ እንዳይፈረድ የኛ የክርስተያኖቹ ወገኖች ከአዳሎችና ከሱማሌ ወገን የተዋጉትን ሲጽፉ የነገሥታቱን የነዓምደ ጽዮንን ፣ የነዘርዓያዕቆብን ጸሐፍተ ትእዛዛቱም አዛዦቹም ሲጽፉ የራሳቸውን ወገን እያጋነኑ የነዚያን እያኩሰሱ እንደዚያው እንዳረብኛው ጸሐፊ የኛም እገሌ (ክርስተያኑ) በእስላሙ (ተንባለት) እጅ ሞተ ምሥጋና ይግባውና (ሎቱ ስብሐት) እያሉ መጻፋቸው የታወቀና የተለመደ ነው ።

ይሁንእንጂ ሙሴ ረኔ ባሴት የተረጐሙት ይህ የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ በኛ በታሪክ ነገሥት ወይም በማናቸውም የታሪክ መጽሐፋችን ውስጥ የማይገኝ የጦርነት ሐተታ ፣ የመሳፍንትና የመኳንንት ታላላቅ የጀብዱ ሥራና ስማቸውን ከሁለቱም ወገን የተደረገውን ውጊያ ደህና አድርጎ ስለሚዘረዝር ለዛሬ ታሪክ ከፍ ያለ ቅም ነገር ያለው ስለሆነ ጸሐፊው ሊመሰገን ይገባል ።

ዳሩ ግን ጽሑፉ ከሥር ዠምሮ እየዘረዘረ በመጻፍ ይመጣና አፄ ልብነ ድንግል እኽያ ዘጠነኛው ዘመነ መንግሥታቸው በተለይ ግራኝ ለመሞት ፳ ዓመት እቀረው ጊዜ ላይ ይኸውም ማለት የጣና ባሕርን ጦርነት ከተረከ በኋላ አቋርጦ ያቆመዋል ። የቀረው ወደፊት የሚገኘው የጦርነት ታሪክ ያዬ ልብነ ድንግል ፍጻሜ ግራኝ ባዬ ገላውዴዎስ ጦርና በፖርቱጋል ጦር ወታደር ተመትቶ መሞቱን አይተርክም ። ይኸንኑ መጽሐፍ ያጠኑና የተረጐሙ ግማሾቹ የግራኝ አህመድ ባለቤት ባቲ ድል ወምበራ የመጨረሻውን ግራኝ ድል የሆነበትን ክፍል ኢቃጠለችው የሚሉ ፣ በድንገተኛ ቃጠሎ ተቃጠለ የሚሉ ጸሐፊው ሳይጨርሰው በመካከሉ ሞተ የሚሉ አሉና ስለ መጨረሻው ታሪክ ጉዳይ የርሱ ሲያቋርጥ የኛ የግዕዙና የፖርቱጋሎቹ ጽሑፍ ስለሚገኝ በማናቸውም ረገድ የጦርነቱ አፈጻጸም ታሪኩ አልጠፋም ።

ስለዚህ የዓረብ ፋቂህንና በዘመኑ የነበሩትን የፖርቱጋል ተወላጆች የነአልቫሬዥን ፣ የነቤርሙዴዝን መጽሐፍ የባሴት ረኔን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ

(1) ሌሎች ደግሞ ዓረብ ፋቂህ ዘሩ የሐረር ተወላጅ ሆኖ ለትምህርት ወደ የመን ሄዶ ቢተ አልፋቂህ በሚባለው ትምህርት ቤት ተምሮ ሊቅ ስለሆነ በዚሁ ዓረብ ፋቂህ ተባለ የሚሉ አሉ ።

እውነተኛውን የግራኝ አህመድን ታሪክ ከየአለበት አጠራቅመን ከዚህ እንደሚከ
ተለው ጽፈነዋል ።

የግራኝ አህመድ አባት ገራድ ኢብራሂም ይባላል ፤ የራሱ ስም አህመድ ያባቱ
ስም ኢብራሂም ኤል ቃዚ ስለሆነ ፤ አድጎ መሪ በሆነ ጊዜ ይማም የሚባለው የማዕ
ርግ ስም እየተጨመረ ይማም አህመድ ቤን ኢብራሂም ይባላል ። በፍጥረቱ ግራኝ
ስለነበር የኛ ሰዎች ግራኝ አህመድ ሱማሌዎች ደግሞ ጉራይ ይሉት ነበር ። ግራኝ
ነቱም በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍና በታሪክ ነገሥት የተረጋገጠ ነው (1) ። አገሩ
ሐባት (ሱማሌ ውስጥ) ነገዱ ከመለሳይ ወገን መሆኑን መለሳይም የሱማሌ ነገድ
መሆኑን ይኸም ነገድ ተዋጊ ጦረኛ መሆኑን ዓረብ ፋቂህ ያረጋግጣል (ገጽ ፹፬ -
፩፻፲፩ - ፩፻፴) ። ይኸም ሐባት ከአዳል ባላባት ከአቡበከር ጋር እየተጣላ ተዋግቶ
ሲሸነፍ እየሄደ የሚደበቅበት አገር ነበር ።

ግራኝ አህመድ የወጣትነቱን ዘመን በገራድ አቡን ቤን አደከ ቤት ማሳለፉ
በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ተመልክቷል ። በዚሁ መጽሐፍ ላይ እንደተመለከተው
ገራድ አቡን በዚያን ሰዓት የአዳልና የዙሪያው ገዥ ነበር ። ግራኝ በገራድ አቡን
ቤት የፈረሰኛ ወታደር ነበር ። እርሱም እንደ አዋቂነቱ ጊዜ በልጅነቱና በወጣት
ነቱ ዘመን ብልህ ጥንቁቅ ምክር አዋቂ ስለነበረ በዚህ ሁሉ ምክንያት ገራድ አቡን
በጣም ይወደው ነበር ።

ነገር ግን ከወላስማ ዘር ከሰዓዲን (ሰአድ፲፮፻ድ - ዲን) የወረደው ዋናው ሱል
ጣን አቡበከር ቤን መሐመድ ገራድ አቡንን አይወድም ነበርና የሱማሌ ጦር አስከ
ትሎ ሊወጋው መጣ ። ገራድ አቡንም ከርሱ ጋር ያሉትን ይዞ ስለ አገሩና ስለወገኑ
በጉብዝና ሲዋጋ ሞተ ። በዚህ ጊዜ የተረፉት የገራድ አቡን ሰዎችና ግራኝ አህመድ
ከአዳል አገር ሸሽተው ወደ ሐባት ሄደው ተቀመጡ ።
ከአዳል አገር ሸሽተው ወደ ሐባት ሄደው ተቀመጡ ። የጦር አለቃ

በዚህ መካከል የታላቁ አውራጃ የደዋሮ ገዥ ያዬ ልብነ ድንግል የጦር አለቃ
ፋኑኤል የአዳልን አገር እየመታ ግራኝ አህመድና ወገኖቹ የገራድ አቡን ሰዎች
ከአቡበከር ሸሽተው እስከተቀመጡበት እስከ ሐባት ደረሰ ። ዓረብ ፋቂህ የዚህን
ውጊያ በሚተርክበት ምዕራፍ ላይ ግራኝ አህመድ ፋኑኤል የአዳልን አገር ሰዉ
ንም እየማረከ ከብቱን ሁሉ እየዘረፈ ሐባት መድረሱን እንደሰማ ወገኖቹን ይዞ
ፋኑኤል ያደረገውን ጥቃት ለመበቀል እንደተጓዘና ከፋኑኤል ጋር አካም ከሚባ
ለው ሥፍራ ላይ መጋጠማቸውን ፤ ፋኑኤልና ጓደኞቹ የጦር አለቆች በሙሉ ብረት
ለበስ የሆነ ጥሩር ለብሰው ከዓይናቸው በቀር የቀረው ሰውነታቸው እንደማይታይ
ይገልጽና የጦርነቱንም ሁኔታ እንደዚህ ሲል ያትታል ። «ጦርነቱ ተዠምሮ ፈረሰ
ኛው ከፈረሰኛ ፤ እግረኛው ከእግረኛ ተደበላልቆ ሲዋጋ አቧራው ሲነሣ በይፍና
ጋሻ እርስ በርሱ እየተማታ ሲጮህ በዚህ ጦርነት ታላቅ የወታደር እልቂት ተደ
ረገ ። በመጨረሻም ክርስቲያኖቹ ተሸንፈው ሸሹ ። እስላሞቹም በዚህ ጦርነት

(1) የዓረብ ፋቂሆን መጽሐፍ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 302 ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 92 ። የልብነ ድን
ግል ታሪክ ገጽ 11 ፤

ብዙ ዕቃና መሣሪያ ከስድሳ ፈረሶች ጋር አገኙ ። በዚህ ዓይነት ግራኝ አህመድና እስላሞቹ በፊት የተማረኩባቸውን ከብቶቻቸውን ሴቶችና ልጆቻቸውን አስመል ሰው በደስታ ወደ ዘፋህ (ዘባን) ተመለሱ» (1) ።

ግራኝ አህመድ ይኸን የመገምገሪያ ድል በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ካለበት ሥፍራ ሐባት (ከደጃ) ድረስ መጥቶ በተዋጋው በደዋሮው ገዥ በፋኑኤል ላይ ካገኘ በኋላ በዚሁ ጊዜ ከዋናው ሱልጣን ከአቡበከር ጋር ተዋግቶ በመገምገሪያ አሸንፎ በመጨረሻ ተሸንፎ ገብሯል ። ዝርዝሩን የሁለቱን የጦርነት ውዝግብ በሚቀጥ ለው ምዕራፍ እስከንመለከት ድረስ አሁን ስለግራኝ አህመድ እነሣሥ በያዝነው ምዕራፍ ውስጥ በነርሱ በኩል በዓረብኛ ቋንቋ ዓረብ ፋቂህ የጻፈለትን እንመል ከት ።

የኢብራሂም ልጅ አህመድ ከሱልጣን አቡበከር በታች እንደ አንድ ኤሚር ሆኖ እየገበረ ሲቀመጥ በዕርቅ ተስማምቶ ወደ ሥፍራው ወደ ሲም ከተመለሰ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ከግዛቱ ከሲም ለአቡበከር የሚገባውን ግብር ይዞ ወደ ሐረር ሔደ ። ሻምንገድ እሚባል ሥፍራ ሲደርስ ጥቁር ደመና የመሰለ ብዙ የንብ መንጋ ከዛፉ ላይ ተነሥቶ የግራኝ አህመድን ጭንቅላት ከቦ እያነበነበ እስከ ሡል ጣኑ ቤት ድረስ አደረሰው ። ወደ ሡልጣኑ ዘንድ ገብቶ ግብሩን ሰጥቶ ተነጋግሮ ሲወጣ እንደዚያው የንቡ መንጋ ከበራፍ ተቀብሎ ፤ እንደከበበው ሳይነድፈው እመ ኖሪያ ቤቱ ድረስ አጅቦት ወደ ቤቱ ሲገባ ንቡም ወደ ዛፉ ተመልሶ ሔደ ። ይኸም የአህመድን የወደፊት ገዥነት ለመግለጽ እግዚአብሔር ያደረገው ተአምራታዊ ምልክት ነው ሲል ዓረብ ፋቂህ እያጋነነ ጽፎታል (2) ።

ከዚህም አያይዞ ሼክ አህመድ የሚባለው ሸሪፍ አቡበከርና ሌላ ደግሞ ታላቅ ሼክ . . . . . ይማም በለው እንጂ ሱልጣንም ኤሚርም በሚባል የማዕርግ ስም አት ጥራው ብለው በሕልሜ ነገሩኝ ብሎ ሼህ መሐመድ ቤን አህመድ እንዳጫወተው ፤ ቀጥሎ ነቢዩ መሐመድ በቀኙ አቡበክር ኤስባዲቄን ፤ በግራው ኡመር ቤን አል ከታብን ፤ በፊቱ አሊ ቤን አቡታሊብን አድርጎ በአሊ ቤን አቡ ታሊብ ግንባር ደግሞ አህመድ (ግራኝ) ነበርና «ማነው ይህ በአሊ ፊት የቆመው» ብሎ አሊ ቤን ሰላህ ነቢዩ መሐመድን ቢጠይቅ «ይህ ወደፊት አበሻን እንዲያስተዳድር ከእግዚአ ብሔር ሥልጣን የተሰጠው አህመድ ነው» ብሎ በሕልሙ እንደመለሰለት ሕል ሙም የታየው ገና አህመድ (ግራኝ) ተራ ወታደር የነበረ ጊዜ መሆኑን ይገል ጻል (3) ።

ይኸን የመሰለው የንብ ተአምራት ፤ የሕልምና የራዕይ ምልክት ብዙ ጊዜ በእ ስያ በአፍሪካ ፤ በአውሮፓም ፤ በክርስቲያኑም ፤ በእስላሙም ቤተ መንግሥት ከጥ ንት ዠምሮ ሲተረክና ሲነገር የቆየ ነው ። ጥንት የግብጾችና የኑብያ ነገሥታት ከክ

(1) ዓረብ ፋቂህ . . . ገጽ 13 - 20
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 21 - 24
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 25 - 28

ርስትና በፊት ይኸን የመሰለ ምልክት ሰጠን የሚሉት እባብንና ዘንዶን ነበር ። ስለዚህም በየዘውዳቸው ላይ የእባብ ምልክት ያደርጉ ነበር ። ይኸም ልማድ በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ ባላባቶች ዘንድ ሳይገባ አልቀረም ። ከንግሥተ ሳባ በፊት አገሩን ዘንዶ «አርዌ ተመን» ይገዛው ነበር ከሚባለው አፈ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ።

የቀረውም በአዕዋፍና በአሞራ ግማሹ በምድር አውሬና እንስሳ የቀረውም በየክፍሉ ሲኖር ከክርስትና ወዲህ ደግሞ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የወረደለትን መሠረት በማድረግ ርግብ ደግሞ ወደዚሁ ወደ እነግሥ ወይም እነጋገሥ ገብታ እገሌ ራስ ላይ ርግብ አረፈችበት ወይም ስታርፍ በሕልሜ አይቻለሁና ይነግሣል እየተባለ ይነገርለት ነበር ። በዚህ ምክንያት የዚህ የንቡ ተአምራት እንደዚሁ በኛም በኢትዮጵያ የዛጔ ቤተ መንግሥት ላዩ ላሊበላ ልደት ተተርኮ ይገኛል ።

ገድለ ላሊበላ የሚባለው መጽሐፍ ስለዚሁ ጉዳይ እንደዚህ ይላል ።

«ላሊበላ በተወለደ ጊዜ ብዙ ንብ መጥቶ ማር ባገኘ ጊዜ እንደሚከብ ጦር ሠራዊት በንጉሡ ዙሪያ እንደሚሰበሰብ እንደዚሁ ንቡ ላሊበላን ከበበው ። ይኸንንም እናቱ ባየች ጊዜ ከእግዚአብሔር የትንቢት መንፈስ ወርዶላት ይህ ሕፃን ትልቅ ሰው ይሆናል ንቦችም ይህ ሕፃን ታላቅ እንደሚሆን አወቁ ብላ ተናግራ በዚሁ የተነሣ ስሙን ላሊበላ ብላ ሰየመችው ፤ ላሊበላ ማለትም ትርጓሜው ንብ ጸጋውን (ጌታውን) አወቀ ማለት ነው» (1) ።

ISIC

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሴም ወይም የካም ዘር ቢሆን አማራና አዳልም ክርስቲያንና እስላምም ቢሆን ልማዱና እምነቱ የሚመራው ባንድ ያስተያየትና የስሜት ዝንባሌ ስለሆነ የግራኝ እንግሥና በንብ መከበብ ክርሱ በፊት ከ፫ መቶ ዓመት አስቀድሞ ከነበረው ካዩ ላሊበላ የልደት ታሪክ ጋር ተጋጠመ ። የላሊበላ ራቅ በማለቱ በዚህም ላይ የዚያን ዘመን ገድል ጸሐፊ ገድሉን እንደ ታሪክ ሲጽፍ ማጣራት ስለማይሆንለት ነገሩን ባይኑ እንዳየ ያህል አረጋግጦ ይጽፋል ። ዓረብ ፋቂህም ባሁኑ በ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ የግራኝን ታሪክ ሲጽፍ በንብ መከበቡን ከሰው ሰምቶ እንደሆነ ነው እንጂ ራሱ ያየ በዚያን ጊዜም ከግራኝ የተገናኘ አይመስልም ። ስለሕልሙ ግን ከእገሌ ሰማሁት እያለ ያወሩትን የሼሆች ስም ጠቅሷል ። ቢሆንም የዚህ ጉዳይ ቢካድም ቢታመንም እንደ አንባቢው ስሜት ነውና አሁን በእኛና በወገኖቹ በኩል ያለውን የግራኝን የዕድገቱንና የእንግሡን ሁኔታ ከአነበብን በኋላ በትክክል ስለልደቱና ስለትውልዱ ሌላ ምርምር እንጨምር ።

(1) ወእመ ወለደቶ እሙ መጽኡ አንህብት ብዙኃን ወአገትዎ ከመ ዘየአግቱ መዓረ ። ወርእያ እሙ እሎንቱ አንህብት ከመ አገትዎ ወኃጸርዎ ለሕፃና ከመ ዘየአውድዎ ሐራሁ ለንጉሥ ፤ ወሶበ ርእየት ዘንተ ወረደ ላዕሌሃ መንፈሰ ተንብዮ ወትቤ ንህብኒ አእመረ ከመ ዓቢይ ውእቱ ዝንቱ ሕፃን ወበእንተ ዝንቱ ሠመየቶ ላሊበላ ንህብ አእመረ ጸጋሁ ብሂል ። ገድለ ላሊበላ ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 12 - 13 ።

## ምዕራፍ ሸ፱

## የግራኝ አህመድ ጉሣውና ትውልዱ ከወዴት ነው ?

ዓፄ ይኩኖ አምላክ በአማራ ዘር እየተረዳ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና በአባ ኢየሱስ ሞዓ እየተደገፈ ከዛጉዌዎች ተረክቦ የመሠረተውን እነ ዓፄ ሠይፈ አርእድ ፣ እነ ዓፄ ዓምደ ጽዮን የገነቡትን ፣ እነዓፄ ዳዊት ፣ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የጣሪውን ውቅር አሳምረው የከደኑትን ብዙ የአማራ ፣ የትግሬ ፣ የአገው ፣ የጸለምት ፣ የዳሞት የባሌ ፣ የደዋሮ ፣ የፈጠጋር ፣ የይፋትና የእንጐት መኳንንትና ሕዝብ ሊቃውንትና መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት የማዕዘን ድንጊያም አሽዋና ሲሚንቶም ሆነው ሁሉም በየበኩሉ ድርሻውን በማበርከት ያጸኑትን ያዒ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለማፈራረስ የቻለው የግራኝ አህመድ አገሩ ወረዳው ጉሣውና ትውልዱ ከወዴት ነው ?

አንድ በጽኑ ምሽግ የተከበበውን ታላቅ የሕንፃ ቤት ለማፍረስ እፍራሹ መድፍ ከነጥይቱ ከዚያ የበለጠ ጠንካራ ኃይል ያስፈልገዋል ። በዚህ አሁን ሲደረግ በምናነበው ጦርነት ግራኝ አህመድ መድፍ ሹማምንቱ ጥይት ሆነው በሚያፈርሱበት ጊዜ ታላቁ የልብነ ድንግል መንግሥታዊ ሕንፃ በዚያው መጠን መላላቱ አብሮ ይታያል ። የዚህን የኃይለኛውን የግራኝ አህመድን ትውልዱን በትክክል ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ስለሆነና ከዚህ ተያይዞም ተለይቶ ስለማይታወቅ ከየሰነዱ ተፈላልገን ከማብራራት ጋር ለአንባቢ ለማቅረብ እንሞክራለን ።

JSIC

ባለፈው ምዕራፍ እንደተረዳነው የግራኝ የአባቱ ስም ከንማዕርጉ ገራድ ኢብ ራሂም ኤል ቃዚ ነው ። በሱማሌ ፣ በአዳል ፣ በባሌ አካባቢ የገራድነት ስም የሚሰጠው ከፍተኛ ባላባትነት ላለው ወይም ችሎቱን በሥራ ላገለጠና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዚያም በዚያው በአዳልና በሱማሌ የጠላስማው መስፍን ለሾሙት የሚሰጥ ነው ።

በዚህ ዓይነት የግራኝ አባት ገራድ ኢብራሂም ከታላላቆቹ የሱማሌ ባላባቶች አንዱ ነበር ማለት ነው ። ጠይቄ እንደተረዳሁት ቃዚ ወይም ካዚ (በሁለቱ አጠራር መካከል ከሃዚ) ማለት ወራሪ (አርበኛ ወይም አዝማች) ስለሆነ የግራኝ ሙሉ ስሙ አህመድ ኢብን ኢብራሂም ኤል ቃዚ ስለሆነ ትርጓሜው የወራሪው ወይም የጦር አዝማቹ የኢብራሂም ልጅ አህመድ ማለት ስለሆነ አባቱ በማዕርግ ስሙ በገራድነቱ ላይ የተዋጊነትና የአርበኝነት ሙያ ያለው ሰው ነበር ማለት ነው ። በዚሁ ምክንያት ይሆናል ከዋናው ሱልጣን ከአቡበከር ጋር ተጣልቶ በመዋጋት እስከ መሞት የደረሰው ። በኋላም የግራኝ አህመድ አሳዳጊ ጌታው አውራይ አቡን የሞተውም በዚሁ ሰበብ ሊሆን ይችላል ።

ዛሬ በሕይወት አንዳንድ የሐረርጌ ሰዎች ከዚያውም ውስጥ በክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ አማካይነት አህመድ አሊ ሻሚን ጠይቄ እንደሚለው የግራኝ አባቱ የሐዊያ ሱማሌ ሐዊያም የሚገኘው በውጋዴን ውስጥ መሆኑን ትውልዱንም እያይዘው ከላይ ሲያመጡት መሐመድ ኡመርን ፣ ኡመር ገራድ ኢብራሂምንና ፈርዳው

ISIC

## ምዕራፍ ጽ፱

## የግራኝ አህመድ ጉሣውና ትውልዱ ከወዴት ነው ?

ዓፄ ይኩኖ አምላክ በአማራ ዘር እየተረዳ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና በአባ ኢየሱስ ሞዓ እየተደገፈ ከዛጉዬዎች ተረክቦ የመሠረተውን እነ ዓፄ ሠይፈ አርእድ ፣ እነ ዓፄ ዓምደ ጽዮን የገነቡትን ፣ እነዓፄ ዳዊት ፣ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የጣሩውን ውቅር አሳምረው የከደኑትን ብዙ የአማራ ፣ የትግሬ ፣ የአገው ፣ የጸለምት ፣ የዳሞት የባሌ ፣ የደዋሮ ፣ የፈጠጋር ፣ የይፋትና የእንጉት መኳንንትና ሕዝብ ሊቃውንትና መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት የማዕዘን ድንጊያም አሸዋና ሲሚንቶም ሆነው ሁሉም በየበኩሉ ድርሻውን በማበርከት ያጸኑትን ያፄ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለማፈራረስ የቻለው የግራኝ አህመድ አገሩ ወረዳው ጉሣውና ትውልዱ ከወዴት ነው ?

አንድ በጽኑ ምሽግ የተከበበውን ታላቅ የሕንፃ ቤት ለማፍረስ አፍራሹ መድፍ ከነጥይቱ ከዚያ የበለጠ ጠንካራ ኃይል ያስፈልገዋል ። በዚህ አሁን ሲያረግ በምናነበው ጦርነት ግራኝ አህመድ መድፍ ሽማምንቱ ጥይት ሆነው በሚያፈርሱበት ጊዜ ታላቁ የልብነ ድንግል መንግሥታዊ ሕንፃ በዚያው መጠን መላላቱ አብሮ ይታያል ። የዚህን የኃይለኛውን የግራኝ አህመድን ትውልዱን በትክክል ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ስለሆነና ከዚህ ቀደምም ተለይቶ ስለማይታወቅ ከየሰነዱ ተፈላልገን ከማብራራት ጋር ለአንባቢ ለማቅረብ እንሞክራለን ።


ባለፈው ምዕራፍ እንደተረዳነው የግራኝ የአባቱ ስም ከነማዕርጉ ገራድ ኢብራሂም ኤል ቃዚ ነው ። በሱማሌ ፣ በአዳል ፣ በባሌ አካባቢ የገራድነት ስም የሚሰጠው ከፍተኛ ባላባትነት ላለው ወይም ችሎቱን በሥራ ለገለጠና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዚያም በዚያው በአዳልና በሱማሌ የወላስማው መስፍን ለሾሙት የሚሰጥ ነው ።

በዚህ ዓይነት የግራኝ አባት ገራድ ኢብራሂም ከታላላቆቹ የሱማሌ ባላባቶች አንዱ ነበር ማለት ነው ። ጠይቁ እንደተረዳሁት ቃዚ ወይም ካዚ (በሁለቱ አጠራር መካከል ከሃዚ) ማለት ወራሪ (አርበኛ ወይም አዝማች) ስለሆነ የግራኝ ሙሉ ስሙ አህመድ ኢብን ኢብራሂም ኤል ቃዚ ስለሆነ ትርጓሜው የወራሪው ወይም የጦር አዝማቹ የኢብራሂም ልጅ አህመድ ማለት ስለሆነ አባቱ በማዕርግ ስሙ በገራድነቱ ላይ የተዋጊነትና የአርበኝነት ሙያ ያለው ሰው ነበር ማለት ነው ። በዚሁ ምክንያት ይሆናል ከዋናው ሱልጣን ከአቡበከር ጋር ተጣልቶ በመዋጋት እስከ መሞት የደረሰው ። በኋላም የግራኝ አህመድ አሳዳጊ ጌታው አውራይ አቡን የሞተው በዚሁ ሰበብ ሊሆን ይችላል ።

ዛሬ በሕይወት አንዳንድ የሐረርጌ ሰዎች ከዚያውም ውስጥ በክቡር ደጃዝማች ወርቅነህ አማካይነት አህመድ አሊ ሻሚን ጠይቁ እንደሚለው የግራኝ አባቱ የሐዊያ ሱማሌ ሐዊያም የሚገኘው በውጋዴን ውስጥ መሆኑን ትውልዱንም አያይዘው ከላይ ሲያመጡት መሐመድ ኡመርን ፣ ኡመር ገራድ ኢብራሂምንና ፈርዳው




የግራኝ አህመድ የ




1. የግራኝ
2. የሱማሌ
3. ሙእኢላ
የግራኝ
ሳህ ትዞ
4. መሐመ
5. ዘሀርቡ
በብዙ
ሞተ ።
6. ሱልጣ
7. የሠራ
8. ከአቡ
9. በደዋ
10. ከኑርና
11. ከሱል

# ግራኝ አህመድ የዘር ግንድ

የዘር ግንድ (ከአረብ ፋቂህና ከአህመድ ሻሚ የተውጣጣ)




ዘመድ ታላቅ ወንድም ራስ ወሰን ሰገድ የገደለው ዓረብ ፋቂህ (ገጽ 227)

› ባላባት የገራድ ማታን ቤን አ.ስማን ሚስት

አህመድ ሻሚ መእንሳ ይልና የኢብራሂም ልጅ የገራድ ካሚል ሚስት ሲያደርጋት ሬኔ ባሴት

ናት ከፃኖ ባሏ የወለደቻት ሳትሆን አትቀርም ይላል (ገጽ 74) ። ኑር የሙጃሂድ ልጅ እናቱ መጂ

ናት

?

ሲዲ ሲዋጋ ኖሮ በአፄ ገላውዴዎስ ዘመን ከክርስቶፎሮስ ደጋማ ጋር በስሜን ሲዋጋ የሞተ ።

ከዚህ በፊት ተማርኮ ዳሞት ሲኖር ከዚያ አምልጦ ሐረር ከገባ በኋላ ከግራኝ ጋር በመገመት

ጋር ግንባር ሲዋጋ ኖሮ ከአምባማሼን አልፎ በትግሬ ጠረፍ (ምንጽ) ሲዋጋ በቀስት ተመትቶ

መሐመድ የሱልጣን አሊ ልጅ የሐርላን ጦር ያዘመተ የሽምብራ ኩሬን ጦርነት የተካፈለ ።

ሹም ተሰፋ ልዑልን የገደለ ከግራኝ ሞት በኋላ ከዔ ገላውዴዎስ ጋር በወጅ ሲዋጋ የሞተ ።

ቺናስ ጋር ተሰውጦ ወደ እናቱ የተመለሰ ።

ዋጋ ተማርኮ አፄ ገላውዴዎስ ፊት የቀረበው ።

ኡስማን ሀበሻው በኋላ የሐረር ሱልጣን ተብሎ የገዛ ።

ጠልያ በኋላ ይማም ተብሎ የገዛ ።

ISIC

ሳን ፤ ገራድ ኢብራሂም ይማም አህመድን (ግራኝን) መውለዱን የነዚህም ሁሉ ከላይ ከሐዊያ በተለይ ከረንሌ ከተባለው የነገድ ቅርንጫፍ መሆኑን ይኸም የነገድ ጐሣ ሠፍሮበት የነበረው በውጋዴን ውስጥ በዚሁ ጐሣ በሚጠራው ቀበሌ መሆኑን ያረጋግጣል ።

የሐዊያ ነገድ በዘመን ብዛት የጐሣው ቅርንጫፍ ተባዝቶ ከሬር ኢብራሂም እስከ ዶጋል (ጀልጀል) ድረስ ቁጥር ፳፺ መድረሱን የሱማሌን ነገድና ባሕል ያጠኑት እነ ባርተን ያመለክታሉ (1) ።

በእውነትም ከዚህ ካፄ ልብነ ድንግል ጋር በሚያደርገው ጦርነት አብዛኛው ጊዜ ታማኝ ሆነው ከተዋጉለት አንዱ ገራድ ማታን ቢን ኡስማን የሱማሌ ባላባት ነው ። እርሱም ወገኑ ከመሆኑ በላይ የግራኝን እህት ፈርዳውሳን ያገባል (2) ።

ግራኝ አህመድ ከአባቱና ከአሳዳጊ ጌታው ከአውራይ አቡን ባላጋራ ከሱልጣን አቡበከር ጋር በተጣላና ከርሱ አደገኛ ውጊያ ለማምለጥ የሚቀመጥበትን ወረዳ ዓረብ ፋቂህ ሆባት (በተለይ ዛካ) የሚባል መሆኑን በታረቀ ጊዜ ደግሞ በሹመት የሚይዘው አገር ሲም የሚባል መሆኑን ያመለክታል ። ሆባት ባዬ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል ። በ፲፫፻፳፭ ዓ. ም. የኡመር ወላስማ ልጅ ሰበርዲን ዋና መሪ ሆኖ ሹክ ሳሊህን አስከትሎ ዓፄ ዓምደ ጽዮንን ለመውጋት በመጣ ጊዜ ለዚህ ውጊያ በውስጡ አስተባብሮ ካመጣቸው በነገሥታት ከሚጠሩት ከ፲፭ የባላባቶች ዝርዝር ውስጥ ፳ኛው የሐርላህ ንጉሥ ፴ነኛው የሆባት ንጉሥ ነው (3) ።

ISIC

ስለዚህ ዛሬ በዘመን ብዛት ቢመነምን ወይም በሌላ ወረዳ ተውጦ ቢጠፋም ሆባት በውጋዴን ውስጥ የነበረ ወረዳ ነው ማለት ነው ። ዛካ ሲም የሚባሉትም ወረዳዎች በዚሁ አቅራቢያ የነበሩት ዛሬ በዘመን ብዛት ሌላ ስም ያግኙ ወይም በዚሁ ስያሜ በቀበሌ ስም ይጠሩ አላውቅም ።

ዓረብ ፋቂህ በጻፈውና ሙሴ ረኔ ባሴት ወደ ፈረንሣዊ በተረጐሙት መጽሐፍ ላይ የግራኝ የነገድ ጐሣ ከ"መለሳይ" ወገን መሆኑን ለማስረዳት እንደዚህ ይላል ።

፩ኛውን "አህመድ" (ግራኝ) ጠሩን ከሦስት ላይ ከፍሎ ፩ኛው ክፍል ሁሉም የሱማሌ ሕዝብ የሆነውን ለገራድ ማታን (ለእማቹ) ሰጠው ፤

፪ኛውን ክፍል የሐርላህን ሕዝብ ለአለቃቸው ለሱልጣን መሐመድ (የግራኝ የእናቱ የእኅት ልጅ ከሱልጣን እሊ የተወለደ) ሰጠው ፤

፫ኛው ለቅዱስ ጦርነት መዋጋትን ልማድ ያደረጉ በውስጣቸው ዝግና አርበኛ የሞላባቸው ከነዚህም አንዱ ይማም (ግራኝ) ያለበት የመለሳይ የጦር ሠራዊት ነው ።

(1) First Footsteps...Chap. V.

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 72 - 73

(3) ያፄ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ገጽ 318

እንግዲህ በዚህ ዓይነት ግራኝ አህመድ የመለሳይ ወገን ነው ማለት ነው ። ግራኝ አህመድ የሚወለድበት የመለሳይ ምናልባትም የዚህ ጐሣ ትክለኛ ነዋሪነቱ በሆባትና በሲም (ው.ጋዴ.ን) ውስጥ ይሆናል ። ሐዊያ የአባት ነገድ ሲሆን መለሳይ ከሐርላህ ወገን የሆነ የእናት ጐሳ ሊሆን ይችላል ። መቼም ያንድ ሰው ባባትና በእ ናት በኩል ቅርንጫፉ ብዙ ነው ።

በኛ በኩል ያለው ተረት ያልተደባለቀበት ሐቀኛውና ባጭሩ የተጻፈው ታሪክ ነገሥት ወደፊት በየምዕራፉ ላይ እንደምናነበው የግራኝ ጐሣ ከመለሳይ ወገን መሆኑን በመግለጽ የዓረብ ፋቂህን አባባል በብዙ ቦታ ላይ አጽድቆት ይገ ኛል ።

ግራኝ አህመድ ወደፊት በንባብ እንደምንደርስበት ዓፄ ልብነ ድንግልን በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ሽምብራ ኩሬ በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ዋስል (ቤተ አምሐራ) እየተዋጋ ካሸነፋቸው በኋላ ንጉሡን እግር በእግር ተከታትሎ ዓባይ ወንዝ ላይ ደርሶ ሊማርካ ቸው ሲል ያመለጡትን ታሪክ ነገሥቱ ባወሳበት ላይ "መለሳይ ከኋላው ተከታ ትሎ በዓባይ ወንዝ ላይ ተገናኙ" ይልና ከዚያ ደግሞ በሌላ ቦታ ላይ ከሰሜን ወደ ደዋሮ መመለሱን ሲያመለክት "መለሳይ ወደ ደዋሮ ሄደ" ቀጥሎም እንጋባ ብሎ ወደ ንጉሡ ላከ ሲል "መለሳይ ወደ ንጉሡ ላከ" በማለት እንዲያውም መለሳይን የግራኝ የመጠሪያ ስም ያስመስለዋል (1) ።

በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ISIG ዝኛው ታሪክ ነገሥት የእስላሞቹን አለቆች ሁሉ መለሳይ እያለ የሚጠራበት ጊዜ አለ ። ለምሳሌ ባንድ ቦታ ላይ "ኡመር የሚባለው መለሳይ ንጉሡን ደግሞ ተዋጋቸው" ይልና በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ "ያገሩ ተወላጅ ኢዮአራም ካንዱ መለሳይ ጋር ሆኖ ንጉሡን ካሉበት ቦታ ተዋግቶ አባረራቸው" ስለሚል እዚህ ላይ ደግሞ መለሳይ የሚባለው ስያሜ ያንድ ክፍል የነገድና የወገን ስም ያደርገዋል ። ይኸም ከዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ጋር በትክክል ይገጥማል (2) ።

ይኸም ግምት ብቻ ሳይሆን ዓረብ ፋቂህ እንዳለው መለሳይ ማለት ግራኝ አህ መድ የሚገኝበት ያንድ ክፍል የጐሣ ስም ነው ። በኋለኛው ዘመን ያፄ ሠርፀ ድን ግልን ዜና መዋዕል ያዘጋጀው ወልደ ሃይማኖት ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን ከአፍ ተል (ዘይላ) ወደብ ገርምሮ እስከ ደኅኖ (አርኪቆ) ድረስ በመላዋ ኢትዮጵያን ወርሮ ከዚያ ደምቢያን ለመኖሪያ መርጦ ከተቀመጠ በኋላ አግብርት የሚባሉትን ሻንቅሎች ሊወጋ ሄዶ ሳይቀናው መመለሱን ለማውሳት እንደዚህ ሲል የጻፈው የበ ለጠ ያብራራል ፤ "ይኸም የሆነው (ግራኝ ሻንቅሎችን ለማስገበር የሞከረው) ከሁሉ በፊት የኢብራሂም ልጅ ኢማም አህመድ በደምቢያ ምድር በነበረበት ጊዜ እርሱም ለመለሳዮች አለቃቸው የሆነውና ከአፍተል ባሕር እስከ ደኅኖ ባሕር ድረስ ሥልጣኑ የተዘረጋው በነበረበት ጊዜ ነው" (3) ።

እዚህ ላይ ወልደ ሃይማኖት አጻጻፉ የሻንቅላ እምቢተኛነት ባፄ ሠርፀ ድን

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92
(2) " " " 93
(3) Historia Regis...C. Rossini. ገጽ 114 - 115

ግል ዘመን ብቻ የተዠመረ ሳይሆን ቀድሞ በግራኝም ጊዜ ደርሶ ነበር ለማለት እግረ መንገዱን በመጥቀስ ታሪኩን ለማበጠር ስለአልፈለገ ግራኝን "የመለሳዮች የበላይ" አለው እንጂ ግራኝ የወገኖቹ የመለሳዮች ብቻ ሳይሆን የመሬሃን የሐብር መጋዲ የሐርላህ የጊሪ በጠቅላላው ከአዋሽ በታች ያለው በልዩ ልዩ ነገድ የተከፋ ለው የአዳልና የመላው ሱማሌ ጠቅላይ የበላይ ነው ።

ከሩቅ የመጡት ፖርቱጋሎች በአጻጻፋቸው ግራኝን አንድ ጊዜ የአዳል ንጉሥ አንዳንድ ጊዜ የወደቡ ከተማ ዘይላ በጣም የታወቀ ስለሆነ የዘይላ ንጉሥ ብለውት ይገኛል (1) ።

በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ግራኝ ኢትዮጵያን ወርሮ ያዬ ልብነ ድንግልን ልጅ አቤቶ ሚናስን ከጦርነት ላይ ማርኮ ወደ ዓረብ አገር ወደ ዘቢድ የላከው ጊዜ የዘቢዱ ፓሻ መስፍኑን ሚናስን ምን ማድረግ እንደሚገባው ቸግሮት ጌታውንና የበላዩን የቱርክን ሱልጣን ሶሊማንን መላከተኞች ልኮ በጠየቀበት ላይ "ሃይማኖቱ ከኛ ጋር የተባበረ የአዳል እስላም አሁን ሀበሻን የሚገዛው የንጉሡን ልጅ ወደኔ ላከው" ብሎ መጻፉን ታሪከ ነገሥት በግዕዝኛው ያነሣል (3) ። በእርሱም አጻጻፍ የግራኝን የአዳል ተወላጅነት ያሳያል ።

ከመሠረቱ ሳይወጣ በሩቅ ያለ ጸሐፊ በወሬ ለጊዜው የገጠመውን ሲጽፍ የፖርቱጋል ተወላጆች ሲጽፉ "የዘይላ ንጉሥ" የዘቢዱ ፓሻ "አዳል" ቢሉ ነገሩ ብዙም አልተራራቀም ፤ አዳልም ዘይላም በዚያ[illegible]ውስጥ ነው ። ነገር ግን ውስጥ አወቆቹ የግራኝ አህመድን ጐሣ በትክክል መለሳይ ያሉትን የኛም መሠረታዊው ታሪከ ነገሥት በብዙ ቦታ እንዳጸደቀው አንብበናል ። በተጨማሪ የመለሳይ ጐሣ በጠባዩ ኃይለኛ ተዋጊ መሆኑን ከነርሱ መካከል ራሱ ግራኝ አህመድ መሆኑን ዓረብ ፋቂህ አስረድተዋል (2) ።

በበኩሉ በሕይወት የሚገኘው አህመድ አሊ ሻሚ የግራኝ አባት ኢብራሂም ኤል ቃዚ ከሐዊያ ጐሣ የሆነ የሱማሌ ተወላጅ መሆኑን ካመለከተ በኋላ ስለ መለሳይ የሐርላህ ነገዶች በመባል የሚጠሩት ምንጫቸው ከኢንዶ እትላንቲክ የመጡ የካም ዘሮች . . . . . . መለሳይ መለሳዮች በመባል የታወቁ ሐረርጌን አቅኚ እንደነበሩና በኋላ በጊዜ ብዛት በጋብቻ በመወረር በሱማሌ በአዳልና በጋላ ተውጠው እንደጠፉ ያረጋግጣል ።

እንግዲህ መደምደሚያውን ግራኝ አህመድ ባባቱ በኢብራሂም የሐዊያ ሱማሌ ተወላጅ በሌላው ወገን (ምናልባት በናቱ) ሐረርጌን ካቀኑት ከሐርላህ የሱማሌ ነገድ በተለይ በአርበኝነት ከታወቁት ከመለሳዮች ወገን ነው ብለን አሳባችንን በዚህ ላይ እናቆማለን ። በእናቱ ወገን የአክስቱ የጋሠ ልጅ ሱልጣን መሐመድ በጦርነት ጊዜ የሐርላህን ነገድ ይዞ መዝመቱ መለሳይ የሐርላህ ቅርንጫፍ መሆኑ ለታሪኩ ደንበኛ መተማመኛ ነው ።

(1) Histoire du Christ. La Croze. ገጽ 114 - 115

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 111.130.185 የሬኔ ባሴት ማስታ. ገጽ 84 ቍ. 4 ።

## ምዕራፍ ፴

## በግራኝ አህመድና በሱልጣን አቡበክር መካከል የተደረገው ጦርነት

## (፲፭፻፲፯ ዓ. ም.)

በዚህ ምዕራፍ ላይ ከግራኝ ጋር ስለተዋጋው ስለሱልጣን አቡበክርና ስለ ዘሩ አመጣጥ በቅድሚያ ማመልከት ታሪኩን ያብራራዋል ። ሁኔታውንም ከሚያብራሩልን የጽሑፍ ሰነዶች አንዱ የአል ማክሪዚና የቼሩሊ ጽሑፎች ናቸው ።

የዓረቡ ጸሐፊ አል ማክሪዚ ኩሬዚት ሌሎቹም ባኑ አብድአል አዳር የቀሩት ባኑ ሐሴም የሚባሉ ከላይ ዘራቸው ከአኪል ቤን አቡ ታሊብ የወረደ በመዠመሪያ ጊዜ ከሄጃዝ (ሄጋዝ) ተነሥተው ጋብራ (ገበርት) በሚባለው በዘይላ ክፍል (ኢትዮጵያ) ከገቡ በኋላ ቀጥለው በአውፋት (ይፋት) ለዘለቄታ ትክለኛ ሆነው ተቀመጡ (1) ። እነርሱም በቁም ነገረኛነታቸውና በደግነታቸው የታወቁ ስለሆነ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከነርሱ መካከል አንዱን ኡመር ወላስማ የሚባለውን የይፋት ከተማና የዙሪያው አገረ ገዥ ብሎ ሾመው ሲል ያረጋግጣል (2) ።

ጸሐፊው ወላስማን የሾመውን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ስሙን አይናገርም ። ነገር ግን የወላስማ ልጆች እነሐቀዲን ፤ እነ ደራደር ከዓፄ ዓምደ ጽዮን (፲፫፻፲፬ - ፲፫፻፵፬ ዓ. ም.) ጋር ስለተዋጉ ከአፄ ዓምደ ጽዮን በፊት የነገሡትም ሰባት ነገሥታት በጠቅላላ የነገሡበት ዘመን ሠላሳ ዓመት ስለማይሞላ ኡመር ወላስማን በይፋት የሾመ ዓፄ ይኩኖ አምላክ (፲፪፻፷፪ - ፲፪፻፸፯ ዓ. ም.) ወይም ተከታይ ልጁ ዓፄ ያግብአ ጽዮን ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ኡመር ወላስማ ገዥነቱን በይፋት በተከለ ጊዜ አምስት ልጆች ወልዶ ዘሩ በገዥነት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ያንዱ የባዚዩ ወገን ነው ። ያምስቱ ስማቸው ደራደር ፤ ሐቀዲን ፤ ባዚዩ (ባዛኡ) ፤ ሑሴይን ፤ ነስረዲን ናቸው ። ባዚዩ ማንሱርንና ገማልዲንን ይወልዳል ። ማንሱር ደልሁይን ፤ ደልሁይ ሰበርዲንን ሰበርዲን አሊን አሊ አህመድ ሐርብ አራድን ሐርብ አራድ ሐቀዲንንና መሐመድ አቡል በራካት ሳዓድ ዲንን ፤ ይወልዳል ። ሰዓዲን ከሌሎች ይበልጥ የታወቀ ስለ ሆነ የነርሱ ግዛት አዳል ይፋት በነርሱ ቋንቋ የሰዓዲን አገር ይባላል ። እንደዚሁም በጐንደር የፋሲል ዘር በሸዋ የሣህለ ሥላሴ ዘር ነኝ ማለት እንደሚያስመካ በአዳልና በይፋት ወላስሞች ዘንድ የሰዓዲን ዘር ነኝ ማለት ያኰራል ።

ይኸው ሰዓድ ዲን በበኩሉ ሰባት ልጆች ይወልዳል ። ከነዚህም በጣም የታወቁት ካፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር የተዋጋው በድላይ ሼሃብ ኢድ ዲን አህመድ (አርዌ በድላይና) አቡበከር ናቸው ። አቡበከር አሊን አሊ አዝሐር አድ ዲንን አዝሐር መሐመድን ይወልዳል ። መሐመድ ዓፄ ልብነ ድንግልና ኤሚር ማኅፉዝ ተዋግተው

(1) አኪል ቤን አቡ ታሊብ የአሊ አባት የነቢዩ የመሐመድ አማችና ዘመድ ነው የእስላም እንሲክሎፔዲ ገጽ 242

(2) Historia Regum. ........17-19

ማኅፉዝ የሞተለት እርሱ አምልጦ የሄደ ነው ። እርሱም አሁን ከግራኝ አህመድ ጋር ተጣልቶ ከመዋጋት የደረሰውን አቡበክርን ይወልዳል ።

በዚህ በአቡበክር ጊዜ (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) የወላስማ ቤት መቀመጫውን ከዳካር (አዳል) ወደ ሐረር አዞረ ። እነዚህ ሁሉ የወላስማ ተወላጆች ሲመቻቸው ካፄ ዓምደ ጽዮን ዠምሮ እስከአሁን እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ድረስ እየሸፈቱ ሳይመቻቸው እየገበሩ ኖረዋል ። ብዙም ጊዜ የባላባትነቱን ሥፍራ የያዘው በንጉሡ ነገሥቱ ላይ ሲሸፍት የሸፍታው ወንድም ታማኝ ሆኖ በንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድ የአዳል ገዥ እየተባለ በመገበር ሲገዛ ኖሯል (1) ።

እንደዚህም ምንም እንኳን የወላስማው ተወላጅ እንደ አንድ መስፍን እንዲያውም እንደ ንጉሥ እየተቆጠረ ፊት ይፋትና አዳል አሁን ሐረርጌ ላይ ተቀምጦ ሡልጣን እየተባለ ቢገዛ በመካከሉ ከሱማሌ ወይም ከአዳል አንዳንድ ቀንደኛ እንደ ኤሚር ማኅፉዝ ወይም እንደ ግራኝ አህመድ ጌታ እንደ ገራድ አቡን እንደ ራሱ እንደግራኝ ያለ ቀንደኛ እየተነሣ ሥልጣን ይፋለማቸዋል ። አንድ አንድ ጊዜም ይፋትና አዳል ለየብቻቸው በየባላባታቸው የተገዙበት ጊዜ አለ ።

ዓፄ ልብነ ድንግልና ኤሚር ማኅፉዝ በ፲፭፻፳ ዓ. ም. ተዋግተው ማኅፉዝ በአባ ገብረ እንድርያስ እጅ የሞተለት ዋናው ሡልጣን መሐመድ ኢብን አዝሐር የደዋሮ እስላሞች ደብቀውት አምልጦ ወደ አገሩ ከገባ በኋላ መሐመድ ኢብን አቡበከርን ኢብን ማኅፉዝ ገድሎት ሥልጣኑን ቀምቶት ነበር (2) ።

ከርሱ በኋላ ደግሞ አውራይ አቡን (የግራኝ ጌታ) ባለሥልጣን ሆኖ ሲያስተዳድር የመሐመድ ልጅ ሡልጣን አቡበክር አውራይ አቡንን ገድሎ በዚሁ ሰበብ በአሁኑ ጊዜ በቀጥታ ከግራኝ አህመድ ጋር ብዙ ጊዜ የጦርነትና የእርቅ ውዝግብ በመካከላቸው ተደርጎ አቡበክር ግራኝ አህመድን ለመግደልም ለማስገደልም ሞክሮ ነበር ። ዳሩ ግን ይኸ ሰው የሐረሩንም ሡልጣን ለመደምሰስ የኢትዮጵያንም የክርስቲያን መንግሥት ለማጥፋት በዕድል የተመደበ ኖሮ ግራኝ በማናቸውም የማይበገር ሆኖ እንዲያውም ግራኝ ሡልጣን አቡበክርን ገድሎ የሚቹን ወንድም ኡመርዲንን በሐረር ላይ አንግሦ እንደልቡ ሙሉውን ሥልጣን ይዞ ይገዛ ዠመር ። ይኸውም በ፲፯፻፳፱ ዓ. ም. ራስ ስሑል ሚካኤል ዓፄ ኢዮአስን አስገድለው ዓፄ ዮሐንስን አንግሠው የጐንደርን መንግሥት ሥልጣን ጨብጠው እንደልባቸው ከገዙት ጋር የሚመሳሰል ነው ።

እንግዲህ በግራኝ አህመድና በሡልጣን አቡበክር መካከል የተነሣው ጠብ እንደኛው አቡበክር የግራኝን አሳዳጊ አውራይ አቡንን በመግደሉ ብቻ ሳይሆን ግራኝ አህመድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ሰውም እያበረለት በመሄዱ ይልቁንም የደዋሮውን ገዥ ፋኑኤልን በጦርነት አሸንፎ ብዙ ምርኮ ማግኘቱ በሡልጣን አቡበክር ዘንድ ጥላቻም ሥጋትም ሊያድርበት ቻለ ። ስለዚህም ሊያጠፋው ተነሣ ። ዳሩ ግን

(1) የኢት. ታሪክ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕራፍ 9 - 35

(2). Studi Etiopici-E-Cerulli: ገጽ 27

ደጃች ካሣ (ቴዎድሮስ) ዝቅተኛ ጦር እስከትለው በተነሡ ጊዜ የጐጃሙ ደጃች ደጃች ካሣ (ቴዎድሮስ) ዝቅተኛ ጦር እስከትለው በተነሡ ጊዜ የጐጃሙ ደጃች ጐሹ ፤ የትግሬው ደጃች ውቤም ዋናው እንደራሴ ራስ ዓሊና እናታቸው እቴጌ መነ ንም በየተራ ካሣን ለማጥፋት ፈትነው እንዳልሆነላቸው አቡበከርም ግራኝን ለማ ጥፋት የሞከረው ሁሉ ሳይሳካ ቀርቶ በመጨረሻ ልክ ለካሣ (ለዓፄ ቴዎድሮስ) እን ደሆነው ሁሉ ይልቅ ግራኝ ሱልጣኑን ሊያጠፋው ቻለ ፡፡

ስለ ሁለቱ ጦርነት ሁኔታውን በቅርብ የተከታተለው ዓረብ ፋቂህ ከዚህ እን ደሚከተለው ያትታል ፡፡

«አህመድ (ግራኝ) ፋትኤልን ድል አድርጎ መመለሱን ሱልጣን አቡበከር በሰማ ጊዜ ደነገጠ ፡፡ ሠራዊቱንም ይዞ ወደ ሱማሌ አገር ወደ ኪዳድ ሔዶ ሠፈረ ፡፡ የዚህን ወሬ ግራኝና ወገኖቹ ሲሰሙ ተከታትለው ሔደው ካርን ከሚባለው ወንዝ ላይ አቡበከርን ገጠሙት ፡፡ አቡበከርና ሱማሌዎቹም ትንሽ እንደ ተዋጉ ሸሹ ፡፡ ከዚህ በኋላ ግራኝ ከነጦሩ ሐረርን ያዘ ፡፡ በኋላ ግን አቡበከር ብዙ ጦር አስከትሎ ወደ ሐረር መምጣቱን ሲሰማ ግራኝ አህመድ ሐረርን ለቆ ወደ ሖባት ዘበርታ ሔዶ ተራራማ በሆነው ሥፍራ ላይ መሽጎ ተቀመጠ ፡፡ ሱልጣን አቡበከር ይኸን ሰምቶ እግር በእግር ተከታትሎ ሔዶ ግራኝ ያለበትን ተራራ ከቦ እስከ አሥር ቀን ድረስ አስጨነቀው ፡፡ ግራኝና ወገኖቹም ተከበው ብዙ ቀን መቆየት ስለሰለቻቸው ከተራ ራው ወርደው ጦርነቱን ገጠሙ ፡፡ ነገር ግን ወዲያው ተሸነፉ ፡፡ . . . . ከዚህ በኋላ ግራኝ ከነሰዉ ታርቆ ለአቡበከር ገባለት ፡፡ አህመድና ጓደኞቹ ለአቡበከር በእርቁ ገብተው ትንሽ ጊዜ እንደቆዩ አቡበከር እርቁን አፍርሶ ሰይፎቻቸውን ቀማቸው ፡፡ ለግራኝም ከ፫ ፈረስ በቀር ምንም አልቀረውም ፡፡ ኡስማን ቤን ያሲን የሚባለው ንም ዋና ኡሚር ገድሎ አገሩን ዘረፈበት ፤ ሌሎቹንም ዳኞችና ሺኮች (ቀሳውስት) በጥላቻ እየጨቆነ አጉላላቸው ፡፡ በዚህ ጊዜ አህመድ ለሕይወቱ ስለፈራ ከሦስት ፈረሰኞቹ ጋር ሌሊት በድብቅ ከአቡበከር አምልጦ ወደ አገሩ ወደ ዛካህ ሔደ ፡፡ በዚያም የአቡበከርን ፬ ፈረሶች ከሚጠብቀው ከሐምዱሽ ቤን ማኅፉዝ (አህመዱሽ የማኅፉዝ ልጅ) ላይ ፈረሶቹን ቀምቶ ዛካህን አገሩን ትቶ ወደ ሌላ ሪባት ኤል ሳካር ወደ ሚባል ዛፍ ወደ ሞላበት በረሃ ሔደ ፡፡ ከርሱም ጋር የነበሩት ፈረሰኞች ሰባት ብቻ ነበሩ ፡፡ ግራኝም ሖባት እሚባለው አገር እስኪገባ ድረስ ከከተማ ወደ ከተማ ብዙ ቀን ሲዘዋወር ቆየ . . . . . . ፡፡

ሱልጣን አቡበከር አህመድን ለመግደል ሲል ሁል ጊዜ ሰላይ እያከታተለ ይልክ ነበር ፡፡ በመጨረሻ አህመድ ሖባት ነው ያለ ማለትን ሲሰማ ገሥግሦ ሔደ ፡፡ በዚያም የአህመድን ቤት አቃጥሎ ብዙ ዕቃ ዘረፈ ፡፡ አህመድም ይኸን ሲሰማ ከሖ ባት ሸሽቶ ወደ ሌላ አገር ሔዶ እየተዘዋወረ ከአቡበከር ወታደሮች ጋር በየጊዜው እየተዋጋ ኖሮ ከዕለታት አንድ ቀን አህመድና ጓደኞቹ በሽሽትና በጉዞ ደክመው ጀዳር እሚባለው ሥፍራ ተኝተው ሳለ አቡበከር ከነወታደሩ ደርሶ ሊፈጃቸው ሲል ድንገት ነቅተው ምንም ሳይሆኑ ሸሹ . . . . . ፡፡ በሖባት ሳለ ኤሚር ሻንባራ የሚ ባል የአቡበከር የጦር አለቃ ከፋኛ ተዋጋቸው ፡፡ ይሁን እንጂ አህመድ አሸ ንፎ አባረራቸው ፡፡ ኤሚር ሻንባራም በጦርነቱ ላይ ሞተ ፡፡ የዚህን ወሬ ሱልጣን

አቡበከር ሲሰማ ፭ ኤሚሮች (መኳንንት) አስቀርቶ ሐረርን ትቶ ከነሠራዊቱ ግራኝን ለማባረር ወደ ሱማሌ አገር ሔደ ። አህመድ አቡበከር አገሩን ለቅቆ መውጣቱን ባወቀና አገር ለመጠበቅ የቀሩትም ኤሚሮች እነማን መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ ወደ ሱልጣን ግዛት ወደ ዛካህ ሔደ ። የአቡበከር እማች ከሹም አቡበከር ከኤሚሮቹ አንዱ ጦሩን አደራጅቶ አህመድ ወደ አለበት አገር ተጓዘ ። በኋላ ግን የአህመድን ጦር ሲያይ ምንም ሳይዋጋ ከነጦሩ ተመልሶ ወደ ሐረር ሸሸ ። አህመድም እሱን ሳይከታተል ከነጓደኞቹ ገሪር እሚባለው ሥፍራ ሆኖ ወደ ሐረር ለመጓዝ ምክር አደረገ ። ብዙዎቹ "ወደ ሐረር ሔደን እንዋጋ እግዚአብሔር ድልን ለፈቀደው ይስጥ" ስላሉ በዚህ ተወስኖ ወደ ሐረር ጉዞአቸውን ዠመሩ ። የተከተላቸው ጦር ፱፻፴ ይደርሳል ።

የሱልጣን አቡበከር ጦር ደጎና ለውጊያ የሚመች ሥፍራ ይዞ ሲጠባበቃቸው አህመድ ከነጦሩ ደረሰና የጠላቱን ጦር አያያዝ ተመልክቶ ምንም ሳይዋጋ ፈርቶ ወደ ኋላው ተመልሶ ወደ አገሩ ይጓዝ ዠመር ። መመለሱን የአቡበከር ጦር በተመለከተ ጊዜ በኋላው ተከታትሎ ሻማ ዝንዱ እሚባለው ሥፍራ ላይ ደረሰበት ። በዚህ ጊዜ አህመድ ከነጦሩ ፊቱን ወደ ጠላቶቹ መልሶ ይዋጋ ዠመር ። ብዙ ጊዜ እንደተዋጉ አህመድ አሸነፈ ። ከአለቆቻቸውም ብዙዎቹን ገደለ ። የቀረውም ጦር ሸሸ ፤ ከመቶ የሚበልጡ ፈረሰኞች ማረከ ። ከዚህ በኋላ ሐረር ገብቶ አገሪቱን በሕግና በሥርዓት ማስተዳደር ዠመረ ። አዋጅ ነጋሪም ወጥቶ "ሁሉም በየቤቱ እንደ ልማዱ ይኑር አትፍሩ ፤ አትዘኑ በማንም ላይ ጥላቻና ቂም የለንም" የሚል አዋጅ እየዞረ አስለፈፈ ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ዋናው የሐረር ሱልጣን አቡበከር በሱማሌ አገር ሆኖ የፈረሰኛና የእግረኛ ጦሩን ከሱማሌ አገር አስከትሎ ወደ ሐረር ተጓዘ ። አህመድም ከሐረር የራሱን ጦር ይዞ አቡበከርን ሊጋጠም ሔደ ። ሁለቱ ባላጋራዎች ዳካር እሚባለው ሥፍራ ተጠጋግተው ሳሉ በመካከላቸው ሽማግሌ ገብቶ ግልግል ዠመረ ። አስታራቂዎቹ ሺሆችና ሕግ አዋቂ ዳኞች ናቸው ። እነርሱም አቡበከር ሱልጣንነቱን እንደያዘ በሐረር የበላይ ሆኖ ገዥነቱን እንዲቀጥል ፤ አህመድ በርሱ ውስጥ የበታች ሹም (ኤሚር) ሆኖ እንዲቀመጥ ስለአስማሟቸው አህመድ ደም ሳይፈስ ዕርቅ በመውረዱ ደስ ብሎት ሱልጣኑ ወደ መቀመጫው ወደ ሐረር ሲሄድ እርሱ ወደ ሲም ሄደ . . . . . » ሲል ዓረብ ፋቂህ ይተርካል (1) ።

ከዚህ በኋላ ነው ይማም ከዕለታት አንድ ቀን በእርቁ መሠረት ግብር ለአቡበከር ይዞ ሲሄድ የንብ መንጋ ከቦት ሸኘው የተባለው (2) ።

ዳሩ ግን ምንም ለጊዜው ቢታረቁ በሁለቱ መካከል ሁል ጊዜ የሥልጣን ሺሚያና የመፈራራት ጉዳይ እንደገና እያመረቀዘ ከመሄድ አላቋረጠም ። እንደልማዱ ግራኝ አህመድ ከብዙ ኤሚሮች ጋር ወደ ደዋሮ መጥቶ ከደዋሮ ክርስቲያኖች ጋር

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 21 - 24
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 17 - 26

ተዋግቶ ፤ ኤሚሮች ቢማረኩበትም እርሱም በበኩሉ ብዙ ምርኮ አግኝቶ ወደ ሐረር እንደተመለሰ ከሱልጣኑ ጋር የነበረው ቂም እንደገና ተቀስቅሶ ሁለቱ ባላጋራዎች ያለፈው እርቅ ምንም ያህል ሳያግዳቸው ሁለቱ ተዋግተው በጦርነቱ ላይ አቡበ ከር ሞተ ። ከዚህ በኋላ የግራኝ ሥልጣን በሐረርና በዙሪያው በደንብ ተመሠረተ ማለት ነው ።

የመጨረሻውን ጠብና ግድያ ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ባጭሩ ያመለክታል «ይማም አህመድ ብዙ ምርኮ ይዞ (ከደዋሮ) እንደተመለሰ በዕርቁ መሠረት ሱልጣኑን ሊገናኘው ቢሄድ ሱልጣኑ አሳቡን ለውጦ ሊገድለው ይፈልግ ዠመር . . . . . ሼኮችም ለእርቅ ቢለምኑት እምቢ ብሎ ይማምን በተንኰል ሊገድለው ተነሣ . . . . ነገር ግን ራሱ ባዘጋጀው የተንኰል ጦርነት ራሱ ሞተ ። ይማም አህመድ እርሱን ገድሎ አገሪቱን ከዚህ ከመጥፎ ሰው አገዛዝ አዳናትና ባገሪቱ ሕግና ሥርዓት እን ዲመሠረት አደረገ . . . . . . በሚቹም እግር ይማም (ግራኝ) የሚቹን ወንድም ኡመር ዲንን ሹሞ የሱልጣንነቱን ሥፍራ እስያዘው» (1) ።

ዓረብ ፋቂህ በአጻጻፉ አቡበከርን መጥፎ ገዥ ሕግ አፍራሽና ያህ በዳይ ሲያደ ርገው ግራኝን ትክክለኛ ሕግ አዋቂ መልካም አስተዳዳሪ ያደርገዋል ። ምክንያቱም ይኸን መጽሐፍ ያዘጋጀው ከአቡበከር ሞት በኋላ ግራኝ በሥልጣን ከተደላደለና ኢትዮጵያንም ለመውረር ችሎ ገዥነቱ በተመሠረተበት ሰዓት ሳይሆን አይቀርም ። በሥልጣን ላይ ያለውን ማሞ[illegible]የርሱን ባላጋራ ማጥላላት በኛም በነርሱም ዘንድ የተለመደ ነው ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ በዚህ ዓይነት ጠብና ጦርነት ከዋናው ሱልጣን ከአ ቡበከር ጋር በነበረበት ሰዓት አፄ ልብነ ድንግልና መኳንንቶቻቸው ከአቡበከር ጋር በመልእክት ተገናኝተው በግራኝ ላይ የኅብረት እርምጃ ሊወስዱ ይችሉ ነበር ። ይኸንንም ቢያደርጉ ግራኝ በሁለቱ ጠላቶች መካከል ሊጠፋ በቻለ ነበር ያሰኛል ። ነገር ግን በዚህ ረገድ ያፄ ልብነ ድንግል መንግሥት ያደረገው ሙከራ ይኑር አይ ኑር አይታወቅም ።

ደግሞም እንደውነቱ ግራኝ ወደፊት በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገውን የተከ ታተለ ጥፋት በዚህ ጊዜ በቅድሚያ መገንዘብ ስለማይችሉ ባለፈውም ግራኝ በፋኑ ኤል ላይ ያገኘውንም ድል ከምንም ስለማይቆጥሩት ለነርሱም የሱልጣኑና የግራኝ ጠላትነት ተመሳሳይና አንድ ስለሆነ የነገሩን ፍጻሜ በተረዳነው በዛሬ አእምሮአ ችን የምንሰነዝረውን የመላ ዘዴ ያን ጊዜ ሊጠቀሙበት አይችሉም ።

እንግዲህ ግራኝ አህመድ የሚጠላውንና የማንቀውን ከወላስማ ከሰዓዲን ዘር የወረደውን ሱልጣን አቡበከርን በዚህ ዓይነት ገድሎ የሚወደውንና የሚያከብረ ውን ኡመር ዲንን በሐረር በሱልጣንነቱ ሥፍራ አስቀምጦ ገዥነቱን ከአደላደለ በኋላ ከኋላው ምንም ሳይሰጋ እንደልቡ ወደፊት ያለውን የኢትዮጵያን ወረራ ያከና ውን ዠመር ። አዲሱ ሱልጣን ኡመር ዲንም በወላስማ ዘርነቱ እንደ አንድ መስ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 31 - 33

ፍን ለስሙ የበላይ ቢመስልም በተግባር ግን በግራኝ አህመድ ሥር ሆኖ ግራኝ ኢ.ት ዮጵያን ለወረረበት ዓላማ ዋና መሣሪያ ሆነ ። ወደፊት እንደምናነበው በግራኝና ባዔ ልብነ ድንግል መካከል ሽምብራ ኩሬ ላይ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በተደረገው ታላቅ ጦርነትና በሌላውም ውጊያ ተካፋይ ሆኖ አብሮ ውሏል ።

## ምዕራፍ ፴፩
## ለግራኝ ድሉን ያከናወኑለት ዋነኞቹ ምክንያቶች ።

የግራኝን የወጣትነቱን ጊዜ እንደምን አሳልፎ እዚህ እንደደረሰ ያገሩንና የነገዱ ንም ክፍል ባለፉት ምዕራፎች ባጭሩ ተገንዝበን ። የወጣትነቱን ጊዜ በገራድ አቡን ቤ.ን አዴክ ቤ.ት አሳልፎ እንዳባት በፍቅር ያሳደገው ጌታው ገራድ አቡን በአቡበከር ሲገደል የጌታውን ጦር ይዞ እንደ ሸፈተና ከጌታው ጠላት ከሡልጣን አቡበከር ጋር አንድ ጊዜ ሲዋጋ አንድ ጊዜ ታርቆ ሲገባ ኖሮ በመጨረሻው አቡበከርን ገድሎ ምንም እንኳን በአልጋው ወንድሙን ማስቀመጡ ባይቀር ከአቡበከር ሞት ወዲህ የሐረርና የዙሪያው ባለሙሉ ሥልጣን መሆኑን ባለፈው አንብበናል ። የአዳልና የሱማሌ ባላባቶችም ራሱ ሡልጣን ኡመር ዲንም በውስጥ ግዛታቸው ነፃ ቢመስ ሉም በጠቅላላው የግራኝ አህመድ አሸናፊነትና ገናንነት እያደገ በመሔዱ ሁሉም በውስጡ ሆነው በርሱ የበላይ አዛዥነት መመሪያ[illegible]ው እርግጥ ነው ።

የአሳዳጊው የገራድ አቡን ገዳይ አቡበከር ባለፈው እንደተገነዘብነው ሲሞ ትና ከፍ ያለው የገዥነት ሥልጣኑ በግራኝ አህመድ እጅ ሲወሰድ በርሱ (አቡበ ከር) አኳያ የነበረውና ዘመዱ ሡልጣን አውራይ አቡን በግራኝና በአቡበከር ጦርነት ጊዜ ሸሽቶ ወደ ሱማሌ አገር ይኖር ነበርና አሁን የግራኝ አህመድን አሸናፊነትና በሥልጣን መደላደሉን በሚቹም በአቡበከር ፈንታ ኡመር ዲን ሡልጣን ተብሎ መሾሙን ሲሰማ ከሸሸበት አገር ከሱማሌ መጥቶ ከግራኝ አህመድ ጋር ታርቆ ገብቶ አገር ተቀብሎ የግራኝ ታዛዥና ጭፍራ ሆነ ። በዘሩ ግንድ ላይ እንባቢ እንደ ሚመለከተው ይህ ሡልጣን አውራይ አቡን ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ በጦርነት ከተገ ደለው ከበድላይ ሺሃብ አድ ዲን አህመድ (ዜና መዋዕላቸው አርዌ በድላይ የሚ ለው) ዘር በቀጥታ የወረደ ነው ። ዝርዝሩም እንደዚህ እያለ ይመጣል ።

በድላይ አህመድ መሐመድ በድላይን ፣ መሐመድ በድላይ ሶለይማን አህመ ድን ፤ ሶለይማን አህመድ ሡልጣን ኡስማንን ፤ ሡልጣን ኡስማን አውራይ አቡንን ይወልዳል (1) ። ስለዚህ እነዚህን ሁለቱም ከዋናው ባላባት ከወላስማ የወረዱትን ሡልጣን አቡበከርንና ሡልጣን አውራይ አቡንን አንዱን በመግደል ካስወገደ አንደ ኛውንም አሳምኖ ካስገበረና የሡልጣንነቱን ሥፍራ ለኡመር ዲን በፈቃዱ ከሰጠ

(1) የኢትዮጵያ ታሪክ ካዔ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 35 ገጽ 184
ፍቱሕ አል ሀበሻ የረኔ ባሴት ትርጉምና ማስታወሻ ገጽ 34 ቊጥር 2 ።

በኋላ ለወደፊቱ በግራኝ ፊት ደፍሮ የገኘነት እሳቡን የሚቃወም ኃይለኛ ባላጋራ አልተገኘም ። ሱልጣን ተብሎ የተሾመው ኡመር ዲን ቢኖግም አልሆነለትም ።

የማኅፉዝን ቤት እንዳይነካበት ባዔ ልብነ ድንግል ጦር አዛዥ በእባ እንድር ያስ እጅ የሞተውን የማኅፉዝ መሐመድን ልጅ ባቲያ ድል ወንበረን በደንብ አግብ ቷል ። ይህቺም ኃይለኛ ሴት ያባቷን ደም ለመበቀል በኢትዮጵያ ንጉሥ ላይ ታጥቃ የተነሣች ናት ። ወንድሟም ገራድ አህመዱሽ በዚሁ ደዞታ የግራኝ አህመድ ዋና ጭፍራ ሆኗል ። በእሁኑ ጊዜ የዘመኑ ባላባቶችና እርሱ እየመለመለ ያሳደጋቸው የጦር አለቆች በርክተዋል ። ስለዚህ በዚሁ ዓይነት ግዛቱም ከሕንድ ውቅያኖስ ዠምሮ እስከ ይፋትና እስከ ባሌ ድረስ ባሉት አገሮች ላይ ተስፋፍቶ የአያሬ የሱ ማሌ የአዳል የኢሳ ነገድ ከነባላባቱ በውስጡ ሲያብርለት ወደፊት ያለው ዋናው ምኞቱ ኢትዮጵያን በሙሉ ለማስገበር ሆነ ።

ይኸን ምኞቱን እላይ እንዳመለከትነው ባጠገቡ ያለችው የሚወዳት ሚስቱ ባቲያ ድል ወንበረ አባቷን ይማም ማኅፉዝን በ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. ያስገደሉትንና ጭን ቅላቱን ያስቆረጡትን ዓፄ ልብነ ድንግልን ለመበቀል እንደምትጐተጉተው አይ ጠረጠርም ። እያት ቅድመ እያቶቻቸው በኢትዮጵያ ነገሥታት ወይም በመኳንን ቶቻቸው ላይ እየሸፈቱ በውጊያ የሞቱት ተማርከው የታሠሩት ሁሉ ባሁኑ ሰዓት ልጆቻቸው ወይም የልጅ ልጆቻቸው በግራኝ ውስጥ ተሰብስበው እንበለው በማ ለት የራሱን የግራኝን የጋለ የወረራ ምኞት እንደሚያጋግሉት የታወቀ ነው ። ቃማማ ላይ ባደረገው ዲስኩር «በመካከላችሁ በክርስቲያን ያልተበደለ ይገኛልን» ቢል ሁሉም «እውነት ነው ከመካከላችን ያልተበደለ የለም» ብለው ጮሁ ሲል ዓረብ ፋቂህ በመጽሐፉ አመልክቷል (1) ።

እንደ ሲዲ አቡበክር ያሉት የቁራን መምህራን የመጻሕፍት ሊቃውንት የክር ስቲያኑን ንጉሥ ወናግ ሰገድን አሸንፎ ኢትዮጵያን ለመውረር ሕዝቡን ለማስለም የሚደረገው ጦርነት ከአላህ (ከእግዚአብሔር) የታዘዘ ከነቢዩ ከመሐመድ የተፈ ቀደ ቅዱስ ጦርነት ነውና በርታ ፤ ጽና እያሉ በቃልም በጽሕፈትም ግራኝን ከነ ጦሩ ከነመኳንንቱ መንፈሱን ለውጊያ ደህና አድርገው አዘጋጁት ። ግራኝ አህመድ ደግሞ ካፄ ልብነ ድንግል የጦር አለቃ ከራስ ደገልሃን ጋር ጦርነት በገጠመበት በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ላይ ዕድሜው ፳፩ ዓመት ስለሆነ ይህ ዕድሜ የወጣትነትና የእ ፍላኔት ጊዜ በመሆኑ በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኝ ጐበዝ የወጣት መሪ ምትን የሚንቅ መሸነፍን የማያምን መንፈሱ ለሥልጣን የሚቸኩል ደሙ በገኘነት ምኞት የፈላ ስለሆነ ይኸ ሁሉ ተጠራቅሞ እስከዚህ ዘመን ድረስ ተፈርቶ ተከብሮ ያዳልን ፤ የይ ፋትን የእስላም ባላባቶች ሲያስገብር የኖረውን በብዙ ዘመናት ዕድሜ የጸናውን የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ መንግሥት ለመገልበጥ ድፍረትን ሰጠው ።

ከዚህ ሁሉ ጋር ልንመለከተው የሚገባን ያዔ ልብነ ድንግልንና የፖርቱጋልን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 156 ቃማማ የሚለው ቃጅማ ይሆን ወይስ ሌላ በባሌ እውራጃ ሌላ በዚህ ስም የሚጠራ ይኖር ይሆን ?

መንግሥት የወዳጅነት ግንኙነት ነው ። በዚያን ዘመን በዓለም የታወቁትና የገነ ኑት ክርስቲያኑ የፖርቱጋልና እስላሙ የቱርክ መንግሥት መሆናቸውን ባለፈው ገልጸናል ። እነዚህ ሁለቱ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ በባሕሩም በየብሱም በወደቡም በግዛትም በጥቅምም በንግድና በሃይማኖትም እየተዋጉ ጠላት ናቸው ። ቱርኮች የኢትዮጵያን ክርስቲያንነትና ነፃ መንግሥትነት አበሻን አትንኩ ያለውን የነቢዩን የመሐመድ ቃል ለማክበር ይሁን ወይም ክርስቲያንም ቢሆን ከግዛታ ችን ከእስክንድርያ ጳጳስ የሚቀበል ከሮማውያንና ከጠላቶቻችን ከካቶሊኮቹ ከፖር ቱጋሎች ጋር የማይጋጠም የተለየ የተዋሕዶ ክርስቲያንነት ያለው ነው ፤ በዚህም ላይ እኛን በሥልጣን በኃይል ለመወዳደር የማይችል ታናሽ መንግሥት ነው በማ ለት ይሁን እስከዚህ ጊዜ ድረስ ምንም እንኳን የዳር ዳሩን ግዛት ምጥዋን አዱሊስን ዘይላን እየኮረኳኮሙ መውሰዳቸው አልፎ አልፎ ማስፈራራታቸውም ባይቀር በጠ ቅላላው አገሩን ለመውረር የታወቀ ጦር አዝምተውበት አያውቁም ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ባዔ ልብነ ድንግል ደብዳቤ ላይ እንደተረዳነው ከፖርቱጋል መልክ ተኞች መምጣት በፊት ከግብፅ ሡልጣኖች ጋር እየተላላከ ከልብም ባይሆን የወዳ ጅነት ግንኙነት አላቋረጠም ነበር ።

አሁን ግን በመጀመሪያው ክፍል እንዳነበብነው ይህ በአጠገባቸው ያለ ጥን ታዊ መንግሥት ሩቅ ከሚገኘው ከጠላታቸው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር መላክ ተኛና ገጸ በረከት እየተለዋወጠ ወዳጅነቱን ሲያጠብቅ ዝም ብለው መመልከት አልሆነላቸውም ። ማኅፉዝ ተዋግቶ በሞተበት ጊዜ (፲፭፻፳፮ ዓ. ም.) ቱርክና ግብፅ እርስ በርስ ከመዋጋት ላይ ስለነበሩ ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ አዙረው ወገናች ውን ማኅፉዝን ለመደገፍ ጊዜ አልነበራቸውም ። አሁን ግን ግብፅ እ. አ. ቆ. በ፲፭ ፻፲፯ ዓ. ም. (፲፭፻፱ ዓ.ም.) በቱርክ ተወሮ በተለይ ባሁኑ ግራኝ በተነሣበት ሰዓት (፲፭፻፲፱ - ፳ ዓ. ም.) የቱርክ መንግሥት ሙሉ ሥልጣኑ የተደላደለበት ጊዜ ስለ ሆነ ኢትዮጵያ ከጠላታቸው ጋር ስትተባበር ዝም ለማለት አልቻሉም ።

ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ምጥዋ የነበረ ጊዜ ኢየሩሳሌም በሚሄዱት በ፲፻፵፰ የኢትዮጵያ ምዕመናን ላይ እስላሞቹ አደጋ ጥለው ከመካከላቸው ከተረፉት ሰዎች ውስጥ አግኝቶ እንደተረዳው «እስላሞቹ እንደዚያ ያጠቋቸው የኛ የፖርቱጊዞች ወዳጆች በመሆናቸው ነው» ሲል አብራርቶ የገለጠውን እናስታውሳለን ።

በዚሁ ጊዜ የግራኝ አህመድ አነሣሥና ድርጅት ስለአጋጠማቸው ለርሱ የዓረ ብና የቱርክ ወታደር አዳዲስ ባዔ ልብነ ድንግል ጦር ዘንድ የማይገኝ የጦር መሣ ሪያ ጠመንጃ ፤ መድፍ ሰጥተው በቅርብ ያለው የግራኝ የግሉ የገዥነት ምኞት በሩቅ ካለው ከቱርኮቹ ዓላማ ጋር ተጋጥሞ ባንድነት እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጽኑና ኃያል የተባለውን ያዔ ልብነ ድንግልን መንግሥት እነሆ ሲገለባብጠው ልንመለ ከት ነው ። የቱርኮች እርዳታ በታሪኩ ውስጥ በርክቶ የምናየው ግራኝና ወገኖቹ በመጀመሪያው ላይ በራሳቸው ተዋግተው ከቀናቸው በኋላ በመካከሉና በመጨረ ሻው የጦርነት ጊዜ ላይ ነው ።

ከዓፄ ልብነ ድንግል ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ የተላኩት አባ ጸጋ ዘአብ ፤ ዶም

ሮድሪግና ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ከዚህ በፊት እንዳልነው ገና ሊሰቦንና ሮማ ሳይደርሱ ግራኝ ጦርነቱን ዝምሮ ዕረፍት ሳይሰጥ ደጋግሞ እየተዋጋ ወረራውን አጋመሰ ። ተመልሰውም መልስ ሳያመጡ በመላው ኢትዮጵያ ላይ ሥልጣኑን ዘረጋ። እንደዚሁ ወደፊት በየምዕራፉ እንደምናገኘው ይህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሕዝብ ዘንድ ጦሩ አርባ ክንድ ሰውነቱ ጋጋኖ ጥይት የትንኝ ያህል የማያመው እየተባለ እንደተረተ የሚነገርለት ግራኝ አህመድ የገራድ ኢብራሂም ልጅ ከደንበኛ ሰውነት ውጭ የሆነ ምንም ጠባይና አካል የሌለው ከማንም መካከለኛ የጦር መሪ የማይበልጥ መሆኑ አይጠረጠርም ። ነገር ግን እላይ ከሰጠነው ሐተታ በቀር ወደፊት በየምዕራፉ እንደምናነበው ለግራኝ ድል አድራጊነትን የሰጡት ምክንያቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ. ግራኝ በፍጥረቱ ብልህነትና ደፋርነት በራሱ ታማኝነት የተዋሐደው ሰው ከመሆኑ ጋር በቅርብ ሆኖ ጦርነቱን ራሱ እየመራ በጥናትና በዘዴ ራሱ እየተዋጋ ጦሩን ማዋጋቱ ፤

፪ኛ. እኔ ያዘዝሁት ብቻ ይፈጸም ሳይል ከውጊያ በፊት ከጦር አለቆቹ ምክርና መላ እየጠየቀ መልካሙን ወገን የመምረጥ ዕድልና ችሎታ ያለው በመሆኑ ፤

፫ኛ. የጠላቱን የጦር ቍጥርና ድርጅት አጥብቆ ሳይመረምርና ለማሸነፉ እርግጠኛ ሳይሆን አብዛኛው ጊዜ ጦርነት አለመግጠሙ (1) ።

፬ኛ. ለፈረሰኛና ለእግረኛ ተዋጊ ጦር የሚመቸውን ሥፍራና ጊዜ እየለየ የማወቅና በሚመቸው ላይ በቆራጥነት ፊት ለፊት ወይም አድብቶ እየጋ ጥሎ የመዋጋት ችሎታ (ፈረንጆች ስትራቴዥና ታክቲክ የሚሉት) ስለ አለው ።

፭ኛ. በምርኮ ላይ አለቆች እንዳይጣሉ ከምርኮ የሚገኘው ሀብት በርሱ ሥልጣን በሙሉ ተሰብስቦ አለቆች ድርሻቸውን ካነሡ በኋላ የቀረው «ቅዱስ ጦርነት» ብሎ ለሠየመው ጉዳይ ብቻ እንዲውል ደንበኛ ሕግ ማውጣቱ ።

፮ኛ. ከሚማረኩት ክርስቲያኖች ውስጥ ጠቃሚነታቸውን ሲመለከት ምሕረት እያደረገ ከነርሱ የጠላትን አሳብና ድርጅት በመጠየቅ ልዩ ልዩ መረጃ እየተቀበለ እነርሱንም እየሾመ ማስደሰቱ ፤ እደገኛነታቸውን ይኸውም ማለት ወደፊት ሲመች ሊከዱ ይችላሉ ብሎ የጠረጠራቸውን ያለርኅራኄ መግደሉ ፤

፯ኛ. በውስጡ ዘመናዊ የጦር መሣሪያና ጠበንጃ የያዙ የጦርነት ዘዴ የሚያውቁ ፤ የቱርክ ፤ የሕንድና የዓረብ ተዋጊዎች ከቀይ ባሕር ማዶ ካሉት አገሮች እየተላላከ ማስመጣቱ ፤

ከዚህ ሁሉ ጋር በጠቅላላው ግራኝ አህመድ እንደሌሎች የክርስቲያኖችና የእስላሞች ታላላቅ መሪዎች በጠባዩ የመሪነት ዕውቀትና ችሎታ ያለው ሰው መሆኑ ይኸን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍ ያለ ሥፍራ የያዘውን የጦርነትና ያሸናፊነት ዕድል ሰጠው ። በመጀመሪያው የጦርነት ዋዜማ ወይም በቅድሚያ በተደረጉት

(1) የሠርፀ ድንግል ዜና መዋዕል አዘጋጅ «ወርእዮ ግራኝ ዘንተ ኵሎ መከረ ምክረ ጠቢብ ..... እስመ የአምር ግብረ ፀብእ .... » በማለት አድናቆቱን ገልጿል ። ገጽ 159

ጦርነቶች ጊዜ በክርስቲያኖቹ ዘንድ በንቀትና በቸልተኝነት መገመቱ ራሱ ለራሱ እንደጠቀመው አይጠረጠርም ።

ስለዚህ ንጉሡ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል የቅርብ አማካሪና የሥራ ጓደኛቸው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ታላላቆቹ የጦርና የአስተዳደር ባለሥልጣኖች ራስ ወሰን ሰገድ ፥ ራስ እስላም ሰገድ ፥ ቢትወደድ ሡርጹ ፥ ራስ ደገልሃን በሐረርጌና በአዳል ትንቢትን ተንተርሶ ይኸን የመሳሰለ ችሎታ ተጐናጽፎ ለበቀል የተዘጋጀውን የግ ራኝ አህመድን አደገኛነት በቅድሚያ የተረዱት በጉዳዩ የሰጉበት ሰግተውም ማጥ ፊያውን ለማዘጋጀት በፍጹም የሞከሩ አይመስልም ። በየጊዜው አንዱ የጦር አለቃ ተዋግቶ ተሸንፎ ሲመለስ ሌሎች ሲደነቁ እንርሱ ደግሞ ገጥመውት ሲሸነፉ የቀ ሩት ሲገርማቸው ይህ የተናቀ የጦር ው ፡ እንደዘበት በየዕለቱ ከድል ወደ ድል እየ ተራመደ በዚያን ጊዜ ላለው መንፈስ በማንም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያልተጠረጠረ ውን ንጉሡ ነገሥቱን እስከማሸነፍ ደረሰ ።

ከንጉሡ መሸነፍ በኋላ የመጣው ራስ ወሰን ሰገድ ደርሶ «በአያቶቻችሁና በአ ባቶቻችሁ ጊዜ አድርገውት የማያውቁትን እነዚህ እስላሞች እንዴት አሸነፏችሁ» እያለ በመገረም ሹማምንቱን ሲወቅስ ግራኝ በሐረርጌ የሚያደርገውን ድርጅት ሱልጣኑን አቡበክርን እስከ መግደል ሲደርስ ሁሉ እርሱንም ሥራውንም በመናቅ ከዚያ አልፎ ኢትዮጵያን ይወራል የሚሉ ጥርጣሬ በጦርነቱ ዋዜማ በማንም ልብ ያደረ አይመስልም ። ያለዚያ ከዚህ በፊት እንዳልነው ግራኝ ከአቡበክር ጋር በሚዋ ጋበት ሰዓት ተደርቦ ለመምታትና ለማስመታት ምቹ ጊዜ ነበር ።

እንግዲህ ከሚቀጥለው ምዕራፍ ገምረን የጦርነቱን ታሪክ በዝርዝር እናነባ ለን ። የታሪኩ ዓይነተኛ መሠረቶች ፪ ናቸው ።

፩ኛ. በዓረብኛ «ፍቱሕ አል ሀበሽ - ትርጓሜው የሀበሻ ወረራ» በሚል አርዕስት በዘያው በጦርነቱ ጊዜ ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ሺሀብ ኤድ ዲን አህ መድ ቤን አብድል ቃድር የሚባለው ባጭሩ ዓረብ ፋቂህ ተብሎ የተሠየ መው የዓረብ ተወላጅ በዓረብኛ ጽፎት ሲኖር ሙሴ ባሴት ሬኔ የሚባሉት ወደ ፈረንሳዊ ተርጉመው በትርጉሙ ላይ ልዩ ልዩ የማስታወሻ ማብራሪያ እየጨመሩ እ. አ. ቆ. በ፲፰፻፺፯ ዓ. ም. ያሳተሙት መጽሐፍ ።

፪ኛ. የዓፄ ኢያሱ አድያም ልጅ የወይዘሮ ወለተ ሩፋኤል ልጅ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ ከየደሴቱና ከየአውራጃው ሰብስበው ከወዳጃቸው ከሸዋው ከአቤቶ አሊጋዝ ጋር የአጠራቀሙት በግዕዝ የተጻፈው ታሪክ ነገሥት ነው ። የዚህ ታሪክ የእጅ ጽሑፍ አንድ ቅጅ በሎንዶን ፥ አንድ ቅጅ በፓሪስ ስለሚገኝ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በቍጥር ፩፻፵፫ ተመዝግቦ ከተቀመጠው ላይ በፎቶ ግልባጩን ወስጄ በእጄ ይገኛል ። ከዚሁ የእጅ ጽሑፍ የውጭ አገር ጸሐፊ ዎች እነሬኔ ባሴት እነገቦል ፔሩሾ እነጐንዜልማን አትመው በመጠኑ አብራ ርተውታል ።

ስለዚህ ወደፊት በሚገኙት ምዕራፎች በየገጹ ግርጌ ቍጥር እየሰጠሁ የምጠ ቅሰው ሙሴ ሬኔ ባሴት ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት የዓረብኛውና ይኸው ታሪክ

ነገሥት መሆኑን ከነዚህም በቀር ሌሎች ለታሪኩ መሠረት የሆኑት ሁሉ አስረጅ ዎች በየገጹ ግርጌ መጠቀሳቸውን አስቀድሜ ለአንባቢ እመለከታለሁ ።

ዓረብ ፋቂህ በጽሑፉ ውስጥ ግራኝን ይማም አህመድ ሲለው እኔ ግራኝ አህ መድ ዓፄ ልብነ ድንግልን ወናግ ሰገድ ወይም ያበሻ ሀፄ የሚለውን የርሱን እንዳጻ ጻፉ መጻፌ ሳይቀር በራሴ አጻጻፍ ውስጥ ዓፄ ልብነ ድንግል ማለቱን እንደዚሁ ዓረብ ፋቂህ በጽሑፉ ውስጥ ከታሪኩ ንግግር ውጭ የራሱን ሐተታ ወይም ከቁራን ብዙ ጥቅስ ሲጨምር አስፈላጊ ከሆነው በቀር የቀረው ትርፍና ጊዜ የሚወስድ መሆ ኑን ተመልክቼ መዝለሌን ፤ ፪ኛ. በአጻጻፉ ውስጥ ሁል ጊዜ እስላሞቹን እግናው ያን ሃይማኖት ያላቸው ክርስቲያኖቹን ኢእማናውያን ሃይማኖት የሌላቸው ወይም በብዙ አማልክት የሚያመልኩ ይል የነበረውን እኔ እስላሞቹን እስላሞች ፣ ክርስቲ ያኖቹን ክርስቲያኖች እያልሁ መጻፌን ፤ ቀጥሎም ዓፄ ልብነ ድንግልን ሽማግ ንት አብዛኛው ጊዜ በጠቅላላ ፓትረስ የሚላቸው ይህ የማስርጣና የሹመት ስም ባገራችን ስላልተለመደ አዝማች አንዳንድ ጊዜ ሹም እያልሁ ከታሪክ ነገሥታችን ጋር እያስተያየሁ መጻፌን ላንባቢ አስገነዝባለሁ ።

ከስም አጠራር ውስጥ በቀጥታ ዓረብኛውን ባለማወቁ ባውቅም ኖሮ ዓረብኛ ውስጥ አንዳንድ በጉሮሮና በላንቃ የሚነገሩ ፊደሎች ባገራችን ፊደል ውስጥ ስለ ሌሉ በጀ በን በከ በቀ መካከል ያለው ድንበኛ አጠራር ተጣርቶ ሊሳካ አይቻልም ። በዚህ ምክንያት በዓረብኛው ላይ ወጀራ ፡ ሙጃሂድ ፡ ራስ ደጃልሃን . . . . . ሲል በግዕዙ ወገራ ሙጋሂድ (አንዳንድ ጊዜ ሙቃሂድ) ራስ ደገልሃን እያለ ይለያያልና በግዕዙ ጽሑፍ ላይ ሊገኝ የቻለውን እንደ ግዕዙ አጠራር እየጻፍሁ አንዳንድ ጊዜም ላንባቢ ግር እንዳይል ያረብኛውን አጠራር በቅንፍ ውስጥ እየጨመርሁ ጽፌዋ ለሁ ።

ISIC

ግራኝ አህመድ በአለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው በሐረርና በአውራ ጃዋ ሥልጣኑ ከመረጋገጡ በፊት በሡልጣን አቡበከር ውስጥ የነበረ ጊዜ ከፋኑኤል ጋር ተዋግቶ መዠመሪያ ፋኑኤል ማሸነፉንና ብዙ ሹማምንት መማረኩን ቀጥሎ ግራኝ ከተማረኩት ውስጥ ብዙ ወንድና ሴት ከብት አስመልሶ በደስታ ወደ አገሩ መመለሱንና በዚሁ ከአቡበከር ጋር ተጣልቶ መዋጋቱ የታወቀ ነው ።

ነገር ግን ሙሉ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ያደረገው የመዠመሪያው ጦርነት ከራስ ደገልሃን ጋር ያደረገው ጦርነት ነው ። በዚህ ምክንያት ያገራችንም ታሪክ ነገሥት የግራኝን የመዠመሪያ ጦርነት የሚያደርገው ይኸንኑ ስለሆነ በሚቀጥለው ምዕ ራፍ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፴፱

## በአፄ ልብነ ድንግል ዳዊትና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገው የመጀመሪያው ጦርነት
## (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.)

እንደ ሺሃብ ኤድን አህመድ ቤን አብድል ቃድር (ዓረብ ፋቂህ) ዝርዝር ታሪክ ባይ ሰጥም የግራኝን ጦርነት ባጫጭሩ የሚያመለክተው በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው ይኸው ያገራችን ታሪክ ነገሥት የግራኝን ጦርነት ሲተርክ ከመጀመሪያው ላይ ከጥ ንት ዠምሮ ኢትዮጵያ ሳትከፈልና የውጭ ገዥ ሳይደፍራት መኖሯን ፡ አንዳንድ የአዳልና የሱማሌ ባላባቶች አድመው በድንገት ቢነሡበትም ዓፄ ዓምደ ጽዮን ሳይ ዘጋጅ አሥሩን ነገሥታት አሸንፎ እንዳስገበራቸው . . . . . እነዚህም በየጊዜው ቢነሡ ነገሥታቱ እነአፄ ሰይፈ አርአድ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ እየወጉ ይመልሷ ቸው እንደነበረ አሁን ግን አገር መደፈር ጠላት መግባት የገርመረው ስመ መንግ ሥቱ ወናግ ሰገድ በሆነው ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን መሆኑን ወናግ ማለትም አን በሳ መሆኑን ይገልጻል (1) ።

ይኸውም አተራረክ እውነት ነው ። ባይሆን ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ በምዕራብ በኑብያ በኩል በምሥራቅ በምጥዋና በአካባቢው በኩል ወደቦቿ እየተያዙ የባሕር ዳር ድንበሯ ይቀርቀፍ እንጂ ከግራኝ በፊት የግሪክ የሮማም የዓረብም የቱማር ችና የከሊፋዎችም በአክሱምም በዛጒዬም ዘመን በኢትዮጵያ የውጭ ወረራ አልገ ባም ። ስሜን አፍሪካ የቀይ ባሕር ማዶ የዓረብ ISIG ሁሉ በነዚህ እላይ በተጠቀ ሱት የቱማር መንግሥታት ሲገዙ ኢትዮጵያ ተወርራ አታውቅም ። የመሬቷ ተራ ራማነት የሕዝቡም ተዋጊነት በጣምም አለመታወቋ ሁሉም ተደራርቦ ምሥጢ ራዊ በሆነ ችሎታ ከወራሪዎች ተርፋ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መቆየቷ እርግጥ ነው ።

ስለዚህ ይኸው ታሪከ ነገሥት ከዚሁ ከላይኛው አተራረኩ አያይዞ ከዚህ በፊት ባለፈው ምዕራፍ እንደተባለው በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. በደዋሮው ገዥ በፋኑኤልና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገውን ከዚያም ወዲህ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ተዋ ግቶ ተሸንፎ መመለሱን ፲ ኤሚሮች (ሹማምንት) እንደተማረኩበት ሳያወሳ አልፎ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት የሠ ራዊቱ አለቃ ደገልሃን ወደ አዳል ዘምቶ ገንዘብና ሴቶቻቸውን ከማረከ በኋላ

(1) ወእስከ ዝ ጊዜ ኢተከፍለት ሀገር ወኢገብአ ፀር ዘይመልክ ባሕቱ እሉ ነገሥታት ይመውዕዎሙ ለብዙኃን ነገሥታት በከመ ሞዖሙ ሐፄ ዓምደ ጽዮን ለ፲ቱ ነገሥታት ሶበ መጽኡ ቦቱ ግብተ እንበለ ያስተጋብእ ሠራዊቶ ባሕቲቱ ግብአተ ሀገርን በእደ ፀር ተወጥነ በዘመነ ንጉሥ ልብነ ድን ግል ወልዱ ለሐፄ ናዖድ ወስመ መንግሥቱ ወናግ ሠገድ ወናግ ብሂል አንበሳ ... ። ታሪክ ነገ ሥት ፓሪስ በቍጥር 143 የተቀመጠው ገጽ 92 ። Etudes Sur l'histoire d'Ethiopie- René Basset ገጽ 327 ።

ግራኝ ተከታትሎ መልሶ በመውጋት ምርኮኞቹንና የተማረከውን ሀብት ማስመለሱን ያመለክታል (1) ።

በደገልሃንና በግራኝ መካከል በዚህ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. የተደረገውን ጦርነት ታሪክ ነገሥቱ የተረከው ዓረብ ፋቂህ ከተረከው ጋር በትክክል ይገጠማል ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ዓረብ ፋቂህ በዓረብኛ በዝርዝር በመግለጥ ወይም የወገኑን ገነን እያደረገ በመተረክ ታሪክ ነገሥቱ በግዕዝና ረዥሙን ታሪካዊ ሁኔታ በማሳጠርና በመቁረጥ ብቻ ነው ።

ነገር ግን የታሪክ ነገሥቱም አጻጻፍ ያንዱ ከሌላው ይለያያል ፤ አንዱ ባጭሩ ሲቆርጥ ሌላው በመጠኑ የሚዘረዝር አንዱ ቀንና ዓመተ ምሕረት ሲጨምር ሌላው የሚዘል አለ ። ከዚህ በላይ ባጭሩ እየጠቀስ የሚያልፈው ሃጃች ኃይሉ እሸቴ (በ፲፯፻፹ - ፹፫ ዓ. ም.) የሰበሰቡትና በውጭ አገር ያሉ ሊቃውንት እነ ባሴት ረኔ ያሳተሙት ሲሆን ከዚህ ደግሞ የቀረው ቢ.ቀር ይኽን የመገርመሪያውን ጦርነት ሰፋ አድርጎ የሚያመለክት ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ግዕዛዊ ታሪክ አለ ። እርሱም ከላይኛው አተራረክ በመስማማትና ሁኔታውን ሰፋ አድርጎ በመጻፍ እንደዚህ ይላል (2) ።

«አፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት ንጉሡ ከየአገሩ ብዙ የጦር ወታደር ሰብስበው የበላይ አዝማች ደገልሃንን አድርገው እንዲዘምት ወደ አዳል አገር ላኩ ። ሠራዊቱም በ[illegible]ት በኩል አድርጎ ሲጓዝ ከብዛቱና ከጩኸቱ የተነሣ በሆዷ ያረገዘችው ሕፃን ጩንግፎ እስኪያስወርዳት ድረስ አንዲት ሴት ደነገጠች ። ደገልሃን አዳል አገር ገብቶ አገሩን ከቦ አስጨንቆ ከብቶቹንም ሰዉንም ፣ ፋጥ የምትባለውን የቀጭኑ አቡበከርንም እናት ጭምር ማረከ ። ያቡበከርም እናት ተማርካ እደገልሃን ፊት በቀረበች ጊዜ "እኔን ብትማርኩ ምን ይጠቅማችኋል ይልቅስ የኔ መያዝ የቃጠሏችሁ ፍጻሜ ይሆናል ። አሸናፊነታችሁም ወደ መሸነፍ ይመለሳል ።

(1) በ፲ቱ ወ፱ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለልብነ ድንግል ንጉሥ ሖረ ደገልሃን መልእከ ኃይሉ ምድረ አዳል ወማኅረከ ንዋዮሙ ወዔወወ አንስቲያሆሙ ወእምዝ ዴገና ግራኝ ወሚጠ ዔዋሁ ወምዛር ካሁ ።

(2) "በ፲ወ፱ቱ ዓመት እመ እመ ነግሠ ፈነዎ ለደገልሃን ወአዘዞ ይሁር ምድረ አዳል ወረሰዮ ምስሌሁ ሠራዊተ ጽኑአነ ወኃያላነ እለ የአምሩ ግብረ ጸብእ ወተቃትሎ አስተጋቢእ እምነ ዙሉ አህጉረ ዊት ብዙኃን ደንገፀት አሐቲ ብእሲት እስከ ድኅፀ ሕፃን ዘውስተ ከርሣ ወሶበ በጽሐ ምድረ አዳል ዓገታ ለሀገር ከመ ነበልባለ እሳት ወጼወወ ዘውስቴታ ሰብአ ወእንስሳ እስከነ እሙ ለቀጭን አቦከር (አቡበከር) ዘትሰሚዩ ፋጥ ወሶበ አብጽሕዎ ኀበ ደጋልሃን ትቤሎ ምንተ ያረብኀክሙ ውዖ ። እስመ ወልድየ ብእሲ ተባዕ ወጽኑዕ ውእቱ ጥቡዕ ልቡ ለቀቲል ። ወበሊህ እንዘ ለክሙ ዝንቱ ቃል ውስተ አፉሃ በጽሐ ግብተ ግራኝ ወወድቀ ላዕሌሆሙ ከመ መብረቅ ውእተ ጊዜ ኃይሉ አፍራሲሆሙ ። ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 327 ። ፓሪስ የተቀመጠው ገጽ 92 ።

ልጇ ጀግና ለጦርነት ልቡ የጸና ፤ እግሩም ደም ለማፍሰስ የፈጠነ ነውና እኔን ሊቃች ሁኝካልሄዳችሁ ከእጃችሁ ሳያድነኝ ልጇ ልቡ እያርፍም'' ብላ ስትናገር ግራኝ በድንገት እንደመብረቅ መጥቶ በላያቸው ወድቆ ተዋጋና ወታደሩም ሁሉ (ክርስቲያኖቹ) ፈረሰኛው ፈረሱን በቅሎኛው በቅሎውን ትቶ ወደኋላም ተመልሶ ልብሱን ሳይዝ ወደቤትም (ድንኳን) ገብቶ ዕቃውን ሳያነሳ ግማሹ በደዋሮ ግማሹ በፈጠጋር የቀረው በይፋትና በግድም መንገድ ሸሸ ። በሠፈር የተገኘው ሰዉም እንስሳዉም በሙሉ በግራኝ እጅ ወደቀ ።የቀጭኑ አቡበክርን እናትም ከክርስቲያኖቹ እጅ አድኗት በታላቅ ክብር ተቀበላትና በከተማቸውም ውስጥ የእስላሞች ወታደሮች በደስታ እንደዚህ እያሉ ግጥም እየገጠሙ ዘፈኑ ፡-

ድል አድራጊ ልጅ ሕዝቡን ለመከላከል ተነሣ ፤
ኃያል ልጅ የተማረኩትን ያገሩን ኃያላን አስመለሰ (አስጣለ)
ተጋዳይ ልጅ የሕዝቡን ገዳዮች በእጥፍ ተበቀላቸው» (1) ።

ዋናው ታሪክ ነገሥት የዘለለውንና ባጭሩ እመዝገመሪያው ላይ ጠቅሶ ያለፈውን ይኸኛው ያፄ ልብነ ድንግል አጭር የግዕዝ ታሪክ ሰፋ አድርጎ እነሆ አሳይቶናል ። ይኸም የግዕዝ ታሪክ ሺሃብ ኤድዲን አህመድ (ዓረብ ፋቂህ) ከጻፈው ሙሴ ረኔ ባሴት ወደ ፈረንሣይኛ ከተረጎሙት ጋር ይስማማል ። ስለዚህ ለአንባቢ ታሪኩ ሙሉ ሆኖ ይገኝ ዘንድ በበኩሉ ዓረብ ፋቂህ ስለዚሁ ጦርነት የሚለውን ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት ።

ISIC

«ጊሪ የሚባል የሱማሌ ነገድ ሜራይሃን (መሪሃን) ከሚባሉት ከጎረቤቱ ከሱማሌ ነገድ (2) ጋር ተጣልተው ሳለ እነርሱን ካስታረቀና (አህመድ) ለርሱም አልገዛም ያሉትን እየወጋ ካስገበረ በኋላ ደገልሃን የሚባል የንጉሥ አማች ከታላላቆች የጦር አለቆች አንዱ በውስጡ ሌሎች የጦር አለቆች አስከትሎ ወደ እስላሞቹ አገር ጠረፍ ወጥቶ መዝረፉን ሀብታቸውንና ሴቶቻቸውን ሁሉ በምርኮ መውሰዱን

ወመስተጽእናነ አብቅልትኒ ኀደጉ አብቅልቲሆሙ ። ዘሀሎ በአፍአ ኢቦአ ኀበ ማኀደሩ ከመ ይንሣእ ዘኮነ ውስተ ቤት ወውስተ ገዳም ሀሎ ኢተመየጠ ድኅሬሁ ከመ ይንሣእ ልብሶ ዝንቱ እንተ ፍኖተ ደዋሮ ፤ ወቦ በፍኖተ ፈጠጋር ወቦ በፍኖተ ኢፋት ወግድም እስመ ፍናዊሆሙ ኮነ ዘዘዚአሁ ። ዘኮነሰ ውስተ ከተማሆሙ ዘተማኅረከኒ እምሀገር ወዘኮነሂ ሎሙ እመ ቀዳሚ አልቦ ዘአምሠጠ እምሰብእ እስከ እንስሳ ዘሎ ገብአ ውስጥ እዴሁ ለግራኝ እስከ እሙ ለቀጭን አቡከር ዘአንገፋ እምእዴሆሙ ወተቀበላ በዓቢይ ክብር እሚሃ ኮነ ፍሥሐ ወሐሤት በከተማሁ ወኮኑ ይብሉ ሠራዊተ እስላም በበሕዘቢሆሙ ።

ወልድ መዊዕ ተንሥአ ቃውመ ለሕዝቡ
ወልድ ኃያል ሰለበ ምህርካ ኃያላን ዘዔወውዋ ለሀገሩ
ወልድ መስተቃትል ፈደየ ምክዕቢተ እምቀታልያነ ሕዝቡ
በብሂለ ዝንቱ ኀለዩ ማኀሌተ ድርሳን ዘይትብሃል ዝክር በልሳነ ብሔሮሙ ።

(1) Storia di Lebne Dingel-C. Rossini ገጽ 9 - 10 19 - 21

(2) መራሂሃን (መሪሃን) በውጋዴንና በሚጁርቲን መካከል የሚገኝ ተዋጊ ሕዝብ ሲሆን ጊሪ ደግሞ በዋርደርና በጅጅጋ የሚገኝ ነገድ ነው ።

ይማም አህመድ ሰማ ። ከምርኮኞቹም መካከል ከኤሚሮቹ ያንዱን የአቡበከር ቀጢን እናት ነበረች ። ጠላት ከ፳፱ የበለጠ የፈረሰኛ ወታደር እንደ እንበጣ የበረ ከተ የእግረኛ ጦር ነበረው ። ይማም አህመድ እነሱን ሊወጋ ተዘጋጀ ። የእስላሞች ጦር ፪፻ ፈረሰኛ ነበር ።

ይማም ፈረሰኞቹን ወደፊት ላካቸው እነርሱም የማታ ጸሎት በሚያረግበት ጊዜ ተነሥተው በማግሥቱ ገጥምበር ስትጠልቅ አካም ከሚባል ወንዝ አጠገብ ደረሱ ። ይማም የጠላትን ጦር ለማሰለል ሰው ልኮ ነበር ። ማንም ወሬ ሊያመጣለት የቻለ የለም ። ከዚህ በኋላ ሁሴን ኤል ጋቱር የሚባለውን ኤሚር (የጦር አለቃ) ከሰባት ፈረሰኞች ጋር ላከው ። እርሱም ወደ ጠላት ሠፈር ተጠግቶ ብዙ መሆናቸውን ሰልሎ ተመልሶ ለይማም አህመድ ነገረው ። ይማም አህመድ ከነጦሩ ወደ ጠላት ተጠጋ በርሱና በጠላቶቹ መካከል የሚያስፈራ ድንጋያማ ተራራ ነበር፤ ይማም ራሱ ከአራት ፈረሰኞች ጋር ወደ ተራራው ላይ ወጣ ። ከርሱም ጋር የነበሩት ፈረሰ ኞች ወዚር ፤ አዶሌ ፤ ኤሚር ባራዳ ፤ ኤሚር አሊ ነበሩ ። እነርሱም እተራራው ላይ ሆነው ቀልቀል ኤዲር (ደፋት) ላይ የሰፈሩትን ጠላቶቻቸውን ተመልከተዋቸው ከዚያ ይማም ወደ ጦሩ ተመልሶ ሌሊቱን ሁሉ ለጦርነት ሲዘጋጅ አደረ ። በማግ ሥቱ የጠላት ጦር ካለበት ተነሥቶ ወደ አገሩ ለመመለስ ሲጓዝ ይማም አህመድ ከኋላ ይከተለው ነበር ። እንደዚህ ተከታትለው ሲሔዱ ከጠላት ወገኖች የሆኑ ሰዎች እስላሞቹን ሲከታተሉአቸው አዩና ለወገኖቻቸው ነገሩ ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ፊታቸውን መልሰው ለጦርነት ተደራጅተው ይጠብቁ ገጠመ ። ይማም አህመ ድም በመካከል በቀኝና በግራ የሚዘምተውን ጦሩን አሰለፈና ወደፊት ተጓዘ ። በመ ጀመሪያ በጠላት ላይ ገሥግሦ ገብቶ ጦርነቱን የገጠመረው ፋራቀሃም ሱልጣን ነው ። እርሱም ገጣሚ የፈረሰኛ ተዋጊ ነውና ''አላህ ታላቅ ነው'' ብሎ ጮሆ ወደ ጠላት ገብቶ ሲዋጋ ወገኖቹም ገብተው ጦርነቱን ገጠሙ ። ፋራቀሃም ሱል ጣን ብዙ ጠላት ገድሎ የጦር አለቃውን የተከላን ልጅ ከፈረሱ ላይ ጥሎ ሰብሮ ማረ ከውና ለይማም አስረከበው ። ይማምም ወደ ዓረብ አገር ላከው ። በዚህ ጊዜ ፈረሰ ኛው ከፈረሰኛ እግረኛው ከእግረኛ ገጥግናው ከገጥግና ጋር ተያባልቆ ሲዋጋ ብዙ ጭንቅላቶች ከሰውነት ላይ እየተቆረጡ ሲወድቁ ብዙ ክንዶች በአየር ላይ ሲበሩ ይታዩ ነበር ። እስላሞቹ ሲፈፈፉ . . . . . መሬት ከነርሱ በታች ትንቀጠቀጥ ነበር . . . . በመጨረሻ ኢአማናውያኑ (ክርስቲያኖቹ) ተበታትነው ሸሹ ። በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰው በዚህ ጦርነት አለቀ ። የኛዎቹ ፈረሱንም በቅሎውንም ሁሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰው በዚህ ጦርነት አለቀ ። የኛዎቹ ፈረሱንም በቅሎውንም ሁሉንም ማረኩ ፤ ፩፻፹፩ ሰው ማረኩ ። ቀድሞ በምርኮ የተወሰደውንም በዚህ ጊዜ አስመልሰው ለየባለቤቶቻቸው አስረከቡ ። ከኛ ምንም ሰው አልተማረከም እንዳ ንድ የቆሰሉትም በቀላል ዳኑ ።

ከዚህ በኋላ ይማም ምርኮኞቹን እፊቱ አስመጥቶ ግማሾቹን ለኤሚር ሶለይ ማን ወደ ዘቢድ ላካቸውና ለርሱ ባሮች ሆኑ ። ግማሾቹንም ገደላቸው . . . . . እንደ ዚህ አድርጎ ይማም በድል አድራጊነት በደስታ በክብር ወደ አገሩ ወደ ሐረር ተመ

ISIC

ለሰ ። በዚህ ጊዜ ይማም ፳፩ ዓመት ሆኖት ነበር» (1) ።

በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ከተደረገው ከፋትኤል ጦርነት ወዲህ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ግራኝ ከራስ ደገልሃን ጋር ያደረገው ይህ ጦርነት በዚህ ዓይነት ይፈጸማል ። ከዚህ በላይ ታሪክ ነገሥቱና ዓረብ ፋቂህ በዝርዝር የሰጡት አተራረክ ይስማማል ።

እዚህ ላይ አስገራሚው ደገልሃን ወደ አዳል ዘምቶ ከምርኮ ጋር ይዟት የመጣው የኤሚር አቡበከር ቀጢን (ቀጭኑ አቡበከር) እናት እኔን መማረክ ምን ይረባች ኋል ልጄ እኔን ከናንተ ሳያስጥል ልቡ አያርፍም . . . . . ያሁኑ ማሸነፋችሁ ወደ መሸነፍ ይመለሳል ያለችው በትክክል መፈጸሙ ነው ። ደገልሃንም ከልክ ያለፈ ጦር ይዞ ማርኮ ሲመለስ እንደምን ተሸነፈ ? እንደምንስ እያደባ ከኋላው የተከተለ ውን የግራኝን ጦር ከኋላው ረዘም ባለ ርቀት ደጀን አድርጎ ንቅቶ በመጠበቅ ተዋግቶ ሳይመልሰው ቀረ ? ሁኔታው ሲገመት በደገልሃንና በሠራዊቱ ዘንድ የጠላትን ጦር ንቀትና ቸልታ ያለ ይመስላል ። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ንቀት ከፍጹም ሞኝነት የሚቆጠር መሆኑ በዚሁ በመሸነፉ ይታወቃል ።

ግራኝ አህመድ ከምርኮኞቹ ውስጥ ግማሾቹን ገድሎ ግማሾቹን ለዘቢዱ አገረ ገዥ ለኤሚር ሶለይማን መላኩ ከዚህ ቀደም እንዳልነው ቱርኮቹ ፤ ግብፆቹ ፤ ዓረ ቦቹ በዚህ ጦርነት ከግራኝ አህመድ ጋር መተባበራቸውን በግልጽ ያሳያል ። ዘቢድ በየመን ውስጥ ከመካና ከሰነዓ በደቡብ በኩል የሚገኝ በዚያን ጊዜ ታላቅ የነበረች የዓረቦች ከተማ ናት ። ግብፅ በማሚሉኮች በም[illegible]በት ጊዜ የመጨረሻው ሱል ጣን ማሚሉክ ካንሱ ኤል ጋውሪ ሶለይማን ራይስን ልኮ አስገብሯት ይኖር ነበር ። በኋላ ደግሞ የግብፅ ማሚሉክ በቱርኮች ኃይል ሲወድቅ ሶለይማን በግዛቱ በዘቢድ በውስጥ አገሩ በራሱ እየተዳደረ ለቱርኮች አምኖ የገባና እየገበረ የተቀመጠ ነው (2) ።

ስለዚህ ዘቢድ በዚህ ዘመን የታወቀች ታላቅ ከተማ ናት ሱልጣኑም (ወይም ፓሻው) የከበረ ነው ። ያዬ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስም ተማርኮ የተላከው ወደ ዘቢድ ፓሻ መሆኑን ወደፊት በዚህ መጽሐፍ ወደ መጨረሻው እንመለከታለን ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ታሪክ ነገሥቱ አፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት ደገልሃን ወደ አዳል ሊዋጋ ሔደ ስለሚል ይህ ዘመን ሺ፭፻፲፱ ዓ. ም. መሆኑ ነው ። የነገሡት በተወለዱ በ፲፩ ዓመታቸው በሺ፭፻፰ ዓ. ም. ስለሆነ ባሁኑ ጊዜ ዕድሜያቸው ፵ ዓመት ደርሷል ማለት ነው ። ግራኝ ግን ዓረብ ፋቂህ እንደጻፈው በዚህ ዓመትና በዚህ ጦርነት ጊዜ ፳፩ ዓመቱ ስለሆነ በዕድሜ ክርሳ ቸው ዘጠኝ ዓመት ማነሱን እንመለከታለን (3) ።

የጦሩን መሪ አዛዥ ደገልሃንን ጽሑፉ ሁሉ ፩ ጊዜ አዛዥ ደገልሃን ፩ ጊዜ አዝ ማች ዲገልሃን ወይም ደልግሐን ወይም ባጭሩ ዴግል ይለዋል ። ዓፄ ልብነ ድንግል

(1) ፍቱሕ አል ሐበሽ - የሐበሽ መሸነፍ — ዓረብ ፋቂህ ገጽ 33 - 34 ።

(2) Studi Etiopici-Storia di Harar-Enrico Cerulli ገጽ 33 - 34

(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 44

በነገሡ በሷ፫ኛው ዓመት ከዚያም በፊትና በኋላ ለአክሱምና ለሌሎች አድባራት ጉልት ሲጕልቱ ስጦታ ሲሰጡ በዚሁ ጊዜ የነበሩትን የቤተ ክህነትና የቤተ መንግ ሥት ሹማምንት ሲጠቅሱ የግራና የቀኝ አዛዦችን ባጠሱበት ጊዜ «ወግራ አዛዚ ዴገልሃን ወቀኝ አዛዚ ይስሐቅ» በማለት በብዙ ቦታ ስሙን እንዶሥተዋል (1) ።

ይኸን መኰንን እስላሞቹ ደጃልሀን ይሉታል ። ግዕዙ መልእክ ኃይል ሲለው በዛሬው ዘመን አጠራር የጦር ሚኒስትር ይኸውም ቢቀር ጠቅላይ የጦር አለቃ እን ደማለት ነው ። የስሙ አጠራር ደገልሃን ሲባል ከሌሎቹ የጦር አለቆችና አገረ ገዥ ዎች ከነፋኑኤል ፣ ከነወሰን ሰገድ ፣ ከነተሰፋ ልዑል የተለየ ስለሆነ ዘሩ እግራና ትግሬ አይመስልም ። ይሁን እንጂ ይህ የጦር አለቃ ባዱ ልብነ ድንግል ቤተ መንግ ሥት የተከበረና የተፈራ የጦር አለቃ ነው ። ሚስቱ ያዱ ልብነ ድንግል እኅት ዓመተ ውጥን ትባላለች ። ግዛቱም በዚያን ዘመን ከታወቁት ከታላላቅ አውራጃ ዎች አንዱ ባሌ ነው ። የቀረውን ታሪኩን ብርታቱንም ፍርሐቱንም ወደፊት በየ ጦርነቱ ምዕራፍ ላይ እንገነዘባለን ።

## ምዕራፍ ፴፫

## በግራኝና በሹማምንቱ (ኤሚሮቹ) መካከል ጦርነቱን የመተውና የመቀጠል ምክር ከአርባ ሺመልና ከወናግ ግISICፎር የተደረገው ጦርነት - ድል ወንበራ ለጦርነቱ ቆርጣ እንደተነሣች (፲፭፻፳፰ ዓ. ም.)

ግራኝ አህመድ ከራስ ደገልሃን ጋር ከመዋጋቱ ቀደም ብሎ ከሱማሌ ባላባቶች ጋር ጠብ እንደገጠመው ለማስረዳት ሲል የራሱ ጸሐፊ ይኸው ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ይገልጻል «ደማም አህመድ ወደ ሀበሻ አገር ለውጊያ በሄደ ጊዜ ሂራቡ የሚባ ለው ሱማሌዎቹን አስከትሎ ወደሐረር ለመምጣት መንገድ ገርምሮ ነበር ። በኋላ ግን የደማምን ወደ ሀበሻ አገር መዝመት ሲሰማ ተመልሶ ወደ አገሩ ገባ ። ከሱማሌ ዎቹም ውስጥ ሀብር የሚባለው ነገድ ለደማም ግብር ከልክሎ መንገድ እየቆረጠ አገርም እየዘረፈ አስቸግሮ ነበር ። ደማም አህመድ ወደነርሱ ዘንድ ተመልሶ አገራ ቸውን እየመታ እነርሱንም ለባሕር የአንድ ቀን መንገድ እስኪቀረው ድረስ አባ ሮሮ ተመለሰ ። . . . . . . በኋላ ግን ሱማሌዎች ሁሉ ሂራቡን ባላባታቸውን ይዘው መጥተው ለግራኝ ገቡለትና እርቅና ሰላም ሆነ» (2) ።

ግራኝ አህመድ ደገልሃንን ማሸነፉና ቀድሞ የተወሰደበትን የሰውና የከብት ምርኮ ማስመለስ በቂው አልሆነም ። በዚህ ምክንያት እንደገና ከከተማው ከሐረር የበረከተ የእግረኛና የፈረሰኛ ጦር አስከትቶ ወደ ፌጠጋር በተለይ ዋዱህ - መሽከ (ዋድሁ መስክ ?) ወደሚባለው ሥፍራ መጣ ። ፌጠጋር የሚባለውን አገር እንባቢ

(1) መጽሐፈ አክሱም — ዘሀገር ወግበዘ አክሱም — ኮንቲ ሮሲኒ ገጽ 38 - 39
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 44 - 45

በካርታው ላይ እንደሚመለከተው ከደዋሮ (የዛሬው ከረዩና የድሬዳዋ አካባቢ)ና ከባሌ በስተ ሰሜን ምዕራብ ያለው ከዛሬው ቡልጋና ምንጃር ዠምሮ እስከ አሩሲ ጫፍ ድረስ ያለው የዛሬው የናዝሬት ግዛት ነው ።

ስለዚህ ካለፈው ከደዋሮው ጦርነት ወዲህ ዓረብ ፋቂህ የሚለውን እንመልከት ።

«ይማም አህመድ ፈጠጋር መጥቶ ዋድሁ መስከ ሰፈረ እርሱና ያበሻ ንጉሥ ባለበት መካከል ያንድ ቀን ተግማሽ የግር መንገድ ይሆናል ። እዚሁ ሥፍራ ሳለ በእስላሞቹ መካከል ምክር ተደረገ ። በምክሩ ውስጥ ይማም አህመድና ግማሾቹ ኤሚሮች ለኛ ድል አድርገን ክርስቲያኖቹን መዝረፍ ወይም ራሳችንን ለሞት ሠውተን መንግሥተ ሰማይን ማግኘት አሳባችን ከነዚህ ከሁለት አንዳቸው ስለሆነ በግሥጋሤ ሄደን በንጉሡ ላይ እንውደቅበትና (አደጋ ጥለን) እንውጋው አሉ ። አብዛኛው የጦር ሠራዊት ግን ይብቃን ወደ አገራችን እንመለስ ፤ እስላሞች በብዙ ምርኮ ከብረዋል አሉ ። ከዚህም የተነሣ ይማም አህመድ ወታደሩ እንመለስ በማለቱ አዝኖ ዓይኑ እስኪቀላ ድረስ አለቀሰ ። ቢሆንም ተመልሶ ወደሐረር ሄደ ።

በሐረር ትንሽ ጊዜ እንደተቀመጠ ይማም አህመድ ለኤሚር ማንሱር ቤን ማኅፉዝ ኤል ጋቱሪ መቶ የፈረሰኛ ሁለት ሺ የግረኛ ጦር ከባንዲራ ጋር ሰጥቶ ወደ አበሻ አገር እስከ ከይጌ ? ድረስ ሄዶ እንዲዋጋ ላከው ። ርሱም ወደዚሁ አገር ደርሶ የሚቋቋመው ጦር ሳያገኝ ብዙ ባሮችና የቀንድ ከብት ዘርፎ ወደ አገሩ ተመለሰ ። እንደዚሁም ሌላ ባንዲራ ለወዚር አዶሌ ሰጥቶ አምስት መቶ የፈረሰኛ ሺ የእግረኛ ጦር ጨምሮ እስከ ደዋሮ በተለይ ወንበሪያ (ወምበራ) ድረስ ዘልቆ እንዲዋጋ አዘዘው ። ርሱም ወደዚሁ አገር ከማንም ሳይዋጋ ደርሶ ብዙ ነገር ማርኮ ሲመለስ የደዋሮ ሰዎች ፈረሰኛውም እግረኛውም ከኋላ ተከታትለው ጦርነት ገጠሙትና ፈረሰኛው ከፈረሰኛ ጀግናው ከጀግና ጋር ተጋጥሞ ይዋጋ ዠመር ። የክርስቲያኖቹ አለቃ አርባ ሺመል (1) የሚባል ረጅም ሰው ነው ። ጦርነቱ ተዠምሮ የጦር መሣሪያ እስኪሰባበር ከንድ እስኪዝል ድረስ ታላቅ ውጊያ በሆነበት ጊዜ ኤሚር ሙጃሂድ የሚባል (የዓሊ ቢን አብደላ ሱሃ ልጅ) . . . . . የጦር አዝማቹን አርባ ሺመልን በኃይል መታና እመሬት ጣለው እንደዚሁም ኑር የሚባለው ሌላውን ሲገድል ትልቅ ውጊያ ከሆነ በኋላ ክርስቲያኖቹ ሸሹ ። ወዚር አዶሌም ምርኮውን ይዞ ወደ ሐረር በደስታ ተመለሰ . . . . . ።

ከዚህ በኋላ ይማም አህመድ ሌላ የጦር ዝግጅት አድርጎ ሲጨርስ ለሁሴን ኤል ጋቱሪ ቀይ ባንዲራና መቶ ፈረሰኛ . . . . . . ለወዚር ኑር (የኢብራሂም ልጅ) ነጭ ባንዲራ ሰጠው ። የራሱ የይማም አህመድ ግን በዚህ ዘመን ባንዲራው ብጫ ነበር ። በእርሱም ዙሪያ ከጐበዛዝቱ ውስጥ ምርጥ የሆኑት በጦርና በሰይፍ የመዋጋት ልምድ ያላቸው ሁለት መቶ ፈረሰኛ ወታደሮች ነበሩት ። የእግረኛው ጦር ሰባት ሺ

(1) ከቁመቱ ርዝማኔ የተነሣ አርባ ሺመል ተብሏል ማለት ነው ። ይኸውም መጠሪያ ስም ሳይሆን የቅጽል ስሙ ነው ማለት ነው ።

ስለሆነ አምስት ላይ ከፍሎ አንዱን በኋላ ወደ ክርስቲያኖች ለዞረውና ክርስቲያን ሆኖ ለሞተው ለናትድያህ ፤ ሁለተኛውን ለአብያል ካሪም ቤን ኡስማን በኋላ ደዋር ተብሎ ለተሰየመው ፤ ሦስተኛውን ለኡመር አብደላ አራተኛውን ለኡስማን ቤን አብደላ ፤ አምስተኛውን ለመሐመድ ሰጣቸው ። እንዚሀንም ሁሉ በውገያ ጊዜ ዝርባቸውን ለጠላት እንዳይመልሱ አደራ አላቸው . . . . . . እንደዚህ ሆኖ ጉዞው ተዠምሮ እስከ ዘሚርዲን ድረስ ዘለቁ (1) ። እዚህ ላይ ሲደርሱ ምክር ተደረገ ሁሉም ደዋሮን እንዝመትበት ብሎ ተስማማ . . . . . ። እስከ ካሃልበሬ (ከሀልበር) ድረስ ግማሹ ጦር ዘልቆ እጠባብ መንገድ ላይ ከክርስቲያኖቹ ጋር ተዋግቶ አሸነፈ ። አንዲት ዛህራቅ የምትባል የቀድሞዎቹ ነገሥታት ያሠሩዋትን ቤተ ክርስቲያን አቃጥለው ተመለሱ ። በዚህ ጊዜ የክርስቲያኖቹ ጦር በቁብ ተሰብስቦ ነበር ቁብ የሚገኘውም በክርስቲያኖቹና በእስላሞቹ አገር መካከል ነበር (2) ። እዚህ አገር ላይ ሲደርሱ እስላሞቹ ምክር አድርገው ግማሾቹ ክርስቲያኖቹን እንውጋ ሲሉ የቀሩት ወደ አገራችን እንመለስ አሉ ። ሌሊቱን አንዳንዶቹ አምልጠው ሲሄዱ ይማም በፈረስ ተከታትሎ በግድ መለሳቸው ።

ቁብ በደረሱ ጊዜ እስላሞቹ ተሰብስበው ሚስትህ ድል ወንበራ ወደ እስላም አገር (ሐረር ) ካልተመለሰች ወደ ሀበሻ አገር እንዘምትም ። ካንተ በፊት የቀደሙት ኤሚሮች አንዱም ሚስቱን አስከትሎ አያውቅም ብለው አመለከቱት ። በዚያን ጊዜ ራሷ ድል ወን[SIC]አልመለስም ብላ እምቢ አለች ። ባለቤቷ ይማም እስከ ይፋት ድረስ ይዟት መጥቶ ከዚያ ሌሊቱን ወደ አበሻ አገር ሄዶ አዋሽ ወንዝ ደረሰ።

አዋሽ ሳሉ ደዋሮ ላይ ስለተገኘው ምርኮ የተዋጋው ሊወስድ ያልተዋጋው ሲቀርበት ክርክር ሆኖ ነበርና . . . . . አሁን አዋሽ ላይ የዚሁ ነገር ተነሥቶ ካለቆቹ ከነገራድ ዲን ጋር ምክር ተደረገና በመጨረሻ ግራኝ ከምርኮው ላይ ፭ኛው ዕጣ ተነሥቶ የቀረው ለማራኪው ይቅርለት የሚል አዋጅ አወጣ ። ከዚሀ በኋላ ብዙውን ጦር እሦስት ላይ ከፍሎ አንዱን ለወዚር አዶሌ ሰጠና በይፋት በቀኝ በኩል እንዲዘምት አደረገው አዶሌ ጥበበኛና ምክር አዋቂ ነው ። ሁለተኛውን ለወዚር ኑር ቤን ኢብራሂም ሰጠና በይፋት በግራ በኩል ዝመት አለው ። ሦስተኛውን ጦር ራሱ ይማም አህመድ ይዞ በመካከል ተጓዘ ።

ወዚር አዶሌ በቀኝ በኩል ሲጓዝ ሳያስበው የክርስቲያኖቹ ሹማምንት ከነወታደራቸው የሰፈሩበትን ሰፈርና ድንኳናቸውን ተመለከተ ። ዋና አለቃቸው ወናግዣን ይባላል ። በክርስቲያኖቹም አነጋገር ትርጓሜው የንጉሥ አንበሳ ማለት ነው ፡ እርሱም የይፋት አገረ ገዥ የሚጠራበት ስም ነው ። ወናግዣን ጀግና ሰው ነበር ፡ እስላሞቹ ክርስቲያኖቹን ሲያዩ ጦርነቱን ዠመሩ ። ከነርሱም መካከል በፊት ክርስቲያን ሆኖ በኋላ ከልቡ ሰልሞ የእስላምን ሃይማኖት ያገለገለው ዠግናው ፋራቃ

(1) ዘሚርዲን የተባለውን ሥፍራ ግዕዝኛው ሰማርማ የሚለው ይመስላል ።
(2) ቁብ የሚለው ቆቦ መሆን አለበት እርሱም በክርስቲያኖችና በእስላሞች አገር መካከል ሲል እሁንም ቆቦ በአዳል አገርና በአማርት በሐራምባ መካከል ይገኛል ።

ሃም ሳቁ የደዋርው በወናግ ዣን ላይ ተወረወረበትና በኃይል መትቶ ጣለው . . . . .
እርሱ ሲሞት ክርስቲያኖቹ ሸሹ ። እስላሞቹ ብዙ ድንኳን የጦር መሣሪያ ፈረስና
ከብት አገኙ ። ከተማረኩት ሴቶችም ውስጥ የንጉሡ የወናግ ሰገድ የእኅት ልጅ ነበ
ረች እርሷንም ይማም አህመድ ለወዚር አዶሌ ሰጠውና ወዳገሩ ወስዷት ነበር
በኋላ ግን ንጉሡ በሃምሳ ወቄት ቀይ ወርቅ ገዝተው አስመለሷት ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ይማም አህመድ የራሱን ጦር ይዞ ከከተማዎቹ ወደ አንዷ፡
ወደ አንጾኪያ ሔደ ለርሱም ሲሙ (ስምዖን) የሚባል በኋላ ሳቅራህ ተብሎ የተሰ
የመ የመንገድ መሪ ነበረው እርሱም እስላም ነበር በኋላ ግን ወደ ክርስትና ዞሮ
ነበር ። በርሱ እየተመራ . . . . . ይማም አህመድ አንጾኪያ ደርሶ አንዲት ቤተ ክር
ስቲያን አገኘ ። ከርሱ ጋር ያሉት ሹማምንት ሁሴን ቢን አቡበከር ኤል ጋቲሪ ፡
ኤሚር አሊ ፡ ገራድ አህሙሽ ፡ ኩሽም አቡበከር ናቸው . . . . ። ይማም አህመድም
ከሚስቱ ከድል ወንበራ ጋር ሆነው ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ውስጡን
ተመለከቱ ሀብት በውስጡ አልተገኘበትምና ወዲያው አቃጥለው ቤተ ክርስቲያ
ኑን አፈረሱት ። በዚህ ጊዜ ከአዶሌ ዘንድ መላክተኛ መጥቶ የወዚር አዶሌን ድል
ማድረግ የወናግ ዣንን መሞት ተናገረና በእስላሞች ዘንድ ትልቅ ደስታ ሆነ ። ደስ
ታቸውንም በከበሮና በተምባል (ነጋሪት) ገለጹ ። ከዚያ በግራ በኩል የዘመተው
ወዚር ኑርም ወዚር አዶሌም አንጾኪያ (ደፋት) ገብተው ከይማም ተገናኙ . . . . .
ከዚያ ይማም ከነጦሩ ከአንጾኪያ ወደ ግንደበሎ በኤሚር አህሙሽ እየተመራ ጉዞ
ዠመረ መንገዱ ጠባብ ስለነበረ ለጉዞ በጣም አስቸጋሪ ነበር . . . . . ከዚህም የተ
ነሣ ሚስቱ ድል ወንበራ በሰው ትከሻ ስትጓዝ ዋለች ። ሲመሽ ጫት በብዙ ከሚገ
ኝበት ዳክ ከሚባል ሥፍራ ሠፈር ሆነ . . . . . ። ሠራዊቱ ሁሉ በጉዞ ደክሞ ስለነ
በረ ራቱን ሳይበላ ጦሙን አደረ ። በማግስቱ በባዝመሉ በኩል አድርገው በሁለተ
ኛው ቀን ግንደበሎ ከሚባለው ከአበሾች አገር ገቡ ። በዚህ አገር ሕዝብ መካከል እስ
ላሞችም ሞልተውበት ነበር ፡ እነርሱም ለአበሻ ንጉሥ እየገበሩ ይኖሩ ነበር ።
አሁን ግን ሺኩና መንደረተኛው ሁሉ ነጋዴውም ወደ ይማም መጥተው አክብረው
ተገናኙት ። ፰ ወቄት ወርቅም እጅ መንሻ ሰጡት ። በዚህ ጊዜ ይማም ደሃ ነበር ሹማ
ምንቱ እነሑሴን ኤል ጋቲሪ እና ወዚር አዶሌ ከዚህ ወርቅ ላይ አንሥተው ለባለ
ቤቱ ለድል ወንበራ ለመስጠት ቢሞክሩ ይማም ይህ ወርቅ በሙሉ ለዚህ ለምናደር
ገው ቅዱስ ጦርነት እስላምን ለመርዳት ወጭ የሚሆን ነው እንጂ ለርሷ የሚሰጥ
አይደለም ብሎ ከለከለ ። አጥብቀው ቢለምኑትም አልተገበረም . . . . ። ወርቁንም
ወደ ሸሪፍ መሐመድ ኢቅ ሻተሪ ልኮ መቶ ሰይፍ አስገዛ በዚያም ሰይፍ እስላሞቹ
በሽምብራ ኩሬ (ወደፊት የሚገኘው) ጦርነት እስላምን በመርዳት መሰከሩበት ።

ይማም ግንደበሎ ሳለ የንጉሡን ሀብት የያዙ ክርስቲያኖች አግኝቶ እነርሱን እከ
ተማው ውስጥ ገድሎ ሀብታቸውንና ከብታቸውን ቀማ ። ከዚያ ከሁለት ቀን በኋላ
የንጉሡን ሀብት እንደያዘ ወደ እስላሞች አገር ተመልሶ አዋሽ ደረሰ ። ከዚያ በብዙ
ችግር ውኃ በማይገኝበት በረሃ አድርጎ . . . . . . በመጨረሻ ሐረር ገባ ። በሐረርም

የምርኮ ክፍያ ሆኖ ፳ተኛውን ዕጣ ሲያነሣ ለርሱ ፳፪ ባርያ ሺ. ከብት ደረሰው። (1) ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሂራብና ሀብር የሚባሉ የሱማሌ ባላባቶች በግራኝ ላይ ሸፍተውበት እንደነበረ በኢትዮጵያ ግዛት በፈጠጋር ሳሉ በምክር ላይ አብዛኛው ከእንግዲህ ወዲያ ጦርነት ይብቃን የምርኮ ሀብትም ጠግበናል ፣ እንግዲህ ወዳገራችን ወደ ሐረር እንመለስ ሲሉ ጦርነት የጠማው ግራኝ በዚሁ ዓይናቸ እስኪቀሉ ድረስ ማልቀሱንና ሳይወድ በግድ ለጊዜው ወደ ሐረር መመለሱን ፣ ጦሩና ሹማምንቱ ከፈጠጋር ወደ ደዋሮ ተላለፈው ግማሾቹ ከአርባ ሺ.መል ግማሾቹ ወደ ይፋት ተዛውረው ከወናግ ግርን ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸውንና በዚሁም ጦርነት የእስላሞቹ መሪዎች ኢማር ሙጃሂድ አርባ ሺ.መልን ፣ ፈራ ታሃም ሳቱ ወናግ ግርንን በቀጥታ አንድ ላንድ እየገጠሙ በመደባደብ እንደገደሏቸው አንብበናል ።

ደዋሮ ውስጥ ወንበራ ወይም ወንበሪያ ከተባለው ሥፍራ ላይ የተዋጋውን አርባ ሺ.መልን ይፋት ውስጥ ዋና የጦር መሪ ሆኖ የተዋጋውን ወናግ ግርንን የሚጠራቸው የመዠመሪያውን በቁመቱ ርዝመት (አርባ ሺ.መል) ሁለተኛውን በልቡ ገርማንነት ወናግ ግርን (የንጉሥ አንበሳ) እያለ በስማቸው ላይ በተሰጣቸው የፈረስ ስምና የቅጽል ስም ይጠራቸዋል እንጂ ለሁለቱም ከጽሑፍ ላይ ሠፍሮ ባለመገኘቱ ልናውቀው ያልቻልነው ሌላ ደንበኛ የመጠሪያ ስም ሳይኖራቸው አይቀርም ።

የይፋቱን ገዥ ወናግ ግርንን ገርማንነቱን ዓረብ ፋቂህ ራሱ በጽሑፉ ገልጾታል ። የጦርነቱን ቦታ ምንም እንኳን በትክክል ለመለየት ባንችል ከዚያው ከይፋት ውስጥ ወይም ከይፋት ወደዚህ ወደ ምዕራብ ገደላማ ያንኮበርና የጉላ ወረዳ ውስጥ ይሆናል ። እነዚህ ወረዳዎች ከአዳል አገር ጋር የሚዋሰኑ ናቸው ። ገደላማነቱን ሲገልጥልን በጉዞ ጊዜ ከዚያ ከጦርነቱ ቦታ ምንም ያህል ባልራቀው በአንጾኪያ ወይም በማንደበሎ ግራኝ ከሚስቱ ከድል ወንበራ ጋር ሲጓዝ ከገደላገደልነቱ የተነሣ የግራኝ ሚስት በከብት ላይ እንኳን መጓዝ አቅቷት በሰው ትከሻ ላይ እንደ ምትጓዝ ተመልክተናል ። አንጾኪያ ግን አሁንም በይፋት ውስጥ እንዳለ ነው ።

ይህ ሳገሩ ሲዋጋ የሞተው የይፋቱ ገዥ ወናግ ግርን ገና ከዓ. ናዖድ ዘመን ዠምሮ አገሩን መከላከል ከለመደው አሁንም በዚያው በልማዱ ወደፊት እንደምናየው ወገኖቹን እየከዳ ለግራኝ መሣሪያ ከሆነው ከራስ ወሰን ሰገድ ወንድም ከወናግ ግርን ጋር ስሙ ስለሚገጥም ሥራቸውና ምግባራቸው ግን ለየብቻ መሆኑን ለአንባቢ እናስገነዝባለን ።

ከዚህም ጋር በዚህ ምዕራፍ ላይ ልንመለከታቸው የሚገቡ ሁለት ጉዳዮች አሉ ።

አንደኛው ግራኝ አህመድ ሂራብ በሚባለው ባላባታቸው መሪነት የሱማሌ ነገዶች በግራኝ ላይ ሸፍተው ግማሾቹ ውጊያ ይቅርብን ሲሉ የቀሩትም መንገድ እየቆረጡ አገሩንም እየዘረፉ ሲያስቸግሩትና ግራኝም በኢትዮጵያ በክርስቲያኖቹ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 44 - 65

ግንባር የገሠመረውን ውጊያ ለጊዜው አቋርጦ ወደነርሱ ተመልሶ ሲዋጋ በዚህ አጋጣሚ ጊዜና ምቹ ምክንያት ዓፄ ልብነ ድንግልና መኳንንቶቻቸው በግራኝ ላይ የሽፈቱን በመርዳት ስለአልተጠቀሙበት ይኸ ቸልተኝነታቸው ግን ለጠላታቸው ለግራኝ ጠቅሞት የነዚያን ሽፍትነት እንደልቡ ደምስሶ ሲመለስ ውጊያውን በነሱ ላይ እንደቀጠለ እንረዳለን ። ዓፄ ልብነ ድንግልና ሹማምንቶቻቸው በመዠመሪያው ከሱልጣን አቡበከር በሚዋጋበት ጊዜ በሁለቱ ጠብ መጠቀም ያልቻሉት አሁንም ከሱማሌዎች ጋር በአደረገው ውጊያ አልተጠቀሙበትም ማለት ነው ።

ሁለተኛ ሴት ወደ ጦርነት አትሄድምና ሚስትህ ድል ወንበራ ወደ አገሯ ትመለስ ብለው ተሰብስበው የእስላሞቹ ሹማምንት ለግራኝ ቢያመለክቱ በ፲፭፻፴ ዓ. ም. በአባ ገብረ እንድርያስ እጅ ጭንቅላቱ ተቆርጦ የሞተውን የሚቸን አባቷን የማኅፉዝን ደም ለመበቀል ቆርጣ የተነሣችውና እንደ ባሏ ጦርነት የናፈቃት ድል ወንበራ እምቢ ብላ ገደላገደሉን በሰው ትከሻ ሜዳውን በከብት እየተጓዘች ጦርነቱን በድፍረትና በግለት መካፈሏን እንመለከታለን ።

እንደዚሁም ከራሱ ከግራኝ አህመድ ገምሮ ያሉት የየነገዱ የጦር አለቆች እንደድል ወንበራ ያለፈ የግዛትን ወይም የዘረፋን ወይም የሞትን በቀል በክርስቲያኖቹ ላይ ለመመለስ ጦር የጠማቸውና ጅሀድ (ቅዱስ ጦርነት) ብለው ተዋግተው ለማሸነፍ ወይም ለመሞት ታጥቀውና ቆርጠው ተዘጋጅተው የተነሡ ሞልተዋል ።

በዚህም ላይ የግራኝ ሹማምንትና ተዋጊዎች ፲፮ቱ ላንድ ከክርስቲያኖቹ ሹማምንት ጋር በሰይፍ መደባደብ በገሠመሩ ጊዜ አብዛኛ ጊዜ የእስላሙ ተዋጊ ስለሚያሸንፍ ባለፉት ዓመታት የእስላሙ ወታደሩም ሹማምንቱም ሁሉ አጥብቆ እመታትንና አመካከትን ሲማር የኖረ ይመስላል ።

በነርሱ አንጻር ያለው ክርስቲያናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የጠላቱን የግራኝና የጦር ሹማምንቱን ድርጅትና ትጥቅ ደህና አድርጎ ሳይገነዘብ የመንፈሳቸውንና የሞራላቸውን ጽናት ሳይመረምርና ማጥፊያውን ወይም መከላከያውን ሳያዘጋጅ በቸልተኝነትና በመናቅ የተለምዶ ኑሮውን በመቀጠል የተቀመጠ ሹማምንቱም በድልወት ሥጋ የከበዳቸው እንጂ ጦርጦራ ተዋጊነት ያላቸው አይመስሉም ። ከሩቅ አገር ዘመደና ደጋፊ ለመሆን የመጡትን ፖርቱጊዞች በቸልታ እስከ ፮ ዓመታት አዘግይቶ የሸኘው ያፄ ልብነ ድንግል መንግሥት አሁንም ከአጠገቡ ከግዛቱ ከአዳልና ከሱማሌ በኩል በዚህ ዓይነት የተቀሰቀሰውን ኃይለኛ የጦር ድርጅት በንቃትና በትጋት ተከታትሎ ከአገሠማመሩ ላይ በቶሎ ሳያጠፋ በመቅረቱ ወደፊት በሚቀጥሉት ዓመቶች ውስጥ በሚያሳዝንና በሚያጸጽት ሁኔታ ራሳቸው ንጉሡ በሽምብራ ኩሬ በሚያስደንቅ አኳኋን ተሸንፈው ሲዋረዱ ፤ በየጊዜው በየተራ ብዙ መኳንንት ከነሠራዊታቸው እየተዋጉ ሲያልቁ ፤ ግራኝም በየቀኑ እንደልቡ ከድል ወደ ድል እየተራመደ አገሩን ሲወር ፤ ሕዝቡን እየፈጀ ሲያሰልም ፤ አብያተ ክርስቲያናቱን ገዳማቱን አስቀድሞ ለውጊያ ለመዘረፊያ መማገር የሚያገለግለውን ጠቃሚና የደለበ ሀብታቸውን እየዘረፈ ሲያቃጥል በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፴፩

### ግራኝ አህመድ ከሸዋ ወደ ሐረርጌ ሄዶ ወታደር በሚመለምልበት ሰዓት ዓፄ ልብነ ድንግል ከባዱቱ ወደቤተ አምሐራ ሄደው ለጦርነት እንደተዘጋጁ (፲፭፻፳ - ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ግራኝ አህመድ በይፋትና በደዋሮ እንዚህን ታላላቅ ድሎች ካገኘ በኋላ ባንድ ወገን ትንሽ ጊዜ ዕረፍት አድርጎ ተዘጋጅቶ ለመመለስ በሌላ ወገን ከዚህ በፊት እንዳል ነው እንመለስ የሚሉትን የሱማሌ ወገኖች ፈቃድ ለመፈጸም አሁንም እንደገና ወደ ሐረር አመራ ። እግረ መንገዱን ግንደበሎ ከተማ ላይ ለንጉሡ ሀብትና ሽቀጥ የሚያመላልሱትን ነጋዴዎች አግኝቶ ገድሎ ሀብታቸውን ከነግማና ከሥጋ ከብታ ቸው ጋር በሙሉ ዘርፎ ጉዞውን መቀጠሉን ፤ ከዚያ እስላሞቹ ሁሉ በአዋሽ ወንዝ አጠገብ አልፈው ሰው እየመራቸው ሲሄዱ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ላይ ሲደርሱ በግራኝ ትእዛዝ ጫካውን በሰይፍ እየመነጠሩ ሲያልፉ በመካከሉ በፊታቸው አቧራ ተነ ሥቶ ወደ አየር ሲወጣ አይተው ጦር መጣብን ብለው ያንግጠው በየፈረሶቻቸው ላይ ወጥተው ለውጊያ ከተሰናዱ በኋላ ሰላይ ዓይቶ መርምሮ ሲመለስ የለም አቧራ ውን ያስነሣው የሚንጋጋ የዝሆንና የድኩላ መንጋ ነው ብሎ ስለነገራቸው የውጊያ መንፈሳቸውን አሳርፈው ጫካውን በሰይፍ እየመነጠሩ አልፈው ሐረር ሊገቡ ጥቂት ሲቀራቸው ዕረፍት አድርገው ግራኝ ከተማረከው ሁሉ ከአምስት አንድ ለራሱ አንሥቶ መውሰዱንና ለራሱ የደረሰው ፳፪ ባሪያ አንድ ሺ ከብት መሆኑን ከዚህ በኋላ በደስታና በድል አድራጊነት ሐረር መግባቱን ዓረብ ፋቂህ ካረጋገጠ በኋላ ከዚሁ አያይዞ ለየባላባቱ ለየነገዱ ከዘረፈው ሀብት እየላከ ለዚህ ቅዱስ ጦር ነት ከርሱ ጋር እንዲተባበሩ በየአለበት በመልእክት ሰብኮ ለሚቀጥለው ጦርነት መዘጋጀቱን ይገልጻል (1) ።

በዓፄ ልብነ ድንግልም በኩል ምንም እንኳን ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ ጽሑፍ ብናጣ ታሪክ ነገሥቱም ሳይጽፈው ቢቀር በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ራስ ደገልሃን በደዋሮ ተሸንፎ ከተመለሰ ወዲህ አሁን ደግሞ በዚሁ ዓመት በ፲፭፻፳ ዓ. ም. አርባ ሺመልና ወናግ ዣን እየተዋጉ ግማሾቹ ሲሞቱ የቀሩት ሲማረኩ ወይም ሲሸሹ እር ሳቸው ዝም ብለው እንደማይቀመጡ የታወቀ ነው ።

ከይፋትና አምላክ ገምሮ እስከ ርሳቸው ጊዜ ድረስ ከአዳል ወይም ከሐረርጌ በኩል የሚቀሰቀሰው ጦርነት በሽፍትነት መልክ አንዱ የወላስማ ባላባት ወይም ቀንደኛ ተነሥቶ አገር ዘርፎ ከብት ነድቶ መመለስ እንጂ ይኸን በመሰለ ቀዋሚ ቶቻቸውም በርሳቸውም ዘመን አጋጥሞ አያውቅም ። በዚህ ምክንያት ነው ታሪክ ነገሥታችን ከመዠመሪያው ላይ "እስከዚህ ጊዜ ድረስ አገሪቱ ተከፋላም የሚገዛ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 65 - 67

ጠላትም ጉብቶባት አያውቅም'' ሲል ያነበብነው ።

በ፲፱፻፷፱ - ፸ ዓ.ም. ላይ የወላስሞቹ ባላባቶች እንሐቀዲን (ሐቅ አድ - ዲን) እነሰበርዲን (ሳብር አድ ዲን) የአዳልንና የሱማሌን ሕዝብ ከነባላባቱ አሥነስተው ቢነሡበት ዓፄ ዓምደ ጽዮን በእንዴት ያለ አኳኋን አሸንፎ እስከ አገራቸው ዳርቻ ደረስ ዘልቆ ምሕረት ተለምኖ በድል አድራጊነት መመለሱን ፤ ከዚያ ወዲህ ቅድም አያታቸው ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የሐቀዲን የወንድም ልጅ መሐመድ ቢን በድላይ በ፲፬፻፴፯ ዓ. ም. ተነሥቶ የደረሰበትን በራሳቸው ዘመነ መንግሥት ከግራኝ አህመድ ፲ ዓመት ቀደም ብሎ የግራኝ ሚስት አባት ኤሚር ማኅፉዝ ቢነሣ ያገኙትን ድል ስለሚያውቁ አሁን ገና ስሙ ባልታወቀ የሱልጣንነት ደረጃ ባልያዘ ይማም አህመድ በሚባል ዓባይ ገነን አዝማችነት የተገፈመረው ጦርነት እስከ መጨረሻ ይቀጥላል ብለው ያሰቡ አይመስልም ።

ምንም እንኳን ባለፉት ሁለት ዓመቶች ያገኙቸውን የጦርነት ድሎች ቢያውቁ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ለታላቁ ንጉሠ ነገሥት እየገበረ የኖረው የአዳልና የሱማሌ ሕዝብ ቢበዛ አገርና ክብት ዘርፎ ወደነበረበት በመመለስ ፈንታ በግራኝ አህመድ ውስጥ ተባብሮ እኔን ከዙፋኔ ለማነቃነቅ ኢትዮጵያን በሙሉ ለመውረር ይመኛል ብለው እርሳቸውም ሹማምንቶቻቸውም የሚያስቡ አይመስልም ። ቢጠረጥሩም አያምኑም ። የጐዳቸውም ይህ በራስ መተማመንና ጠላትን አለመጠርጠር ነው ።

ISIC

በዚህም ላይ ጥርጣሬም ቢኖር ይኸንኑ ወረራ ለመመለስ የሚችል ብዛቱም ዝግጁነቱም የሚያኮራ በያለበት ያላቸው የሸዋ ፥ የትግሬ ፥ የበጌምድር ፥ የጎጃም ፥ የባሌ ፥ የደዋሮ ጦር ከነሹማምንቱ መመከት ብቻ ሳይሆን በሽፍታና በዘራፊ ስም የሚጠሩዋቸውን አዳሎችን እስከ ሐረር ድረስ ዘልቆ እንደሚቀጣላቸው ሳይተማመኑ አልቀረም ። ዳሩ ግን በዚህ ዓለም ማናቸውም ነገር ተለዋዋጭ ነው ። የሕዝብና የተዋጊ መንፈስ የድልም ዕድል እንዳዘጋጁትና እንደተገበት መጠን ፍሬውን ይሰጣል ።

በማናቸውም ደረጃና ዓይነት የሚገኘውን ጠላት መናቅ ወይም ችላ ማለት እንደማይገባ ይህ የግራኝ አነሣሥና ያዒ ልብነ ድንግል ውድቀት በሌላውም አገር የሚደርሰው ይኸን የመሳሰለው አድራጎት ትምህርት ይሰጣል ። የሰው ልጅ ግን በጉብዝናውና በተንኮሉ በብልህነቱና በትጋቱ ላይ ዝንጋኤና ንቀት ስለተበረዘበት ታሪክ በሚሰጠው ትምህርት ከሚጠቀመው የማይጠቀመው ይበልጣል ። በታሪክ ትምህርት እንጠቀም የሚሉ ቢኖሩ ቊጥራቸው ያንሳል ፤ ቊጥራቸው ያነሰውም ቢናገሩ ቢመክሩ በብዙዎቹና በታላላቆቹ ዘንድ አድማጭና ተቀባይ ላያገኙ ይችላሉ ። በመምከራቸውም ምክራቸው አልሰማ እያለ በዚሁ ቢበሳጩና ቢነጫነጩ ጥላቻን ሊያተርፉ ይችላሉ ። መከራው ከደረሰና ምንም ለማድረግ በማይቻልበት ጊዜ እነእገሌ እኮ እንደዚህ ብለው ነበር ቢባል ትርፉ ጸጸትና ንዴት ነው ። ዠኔራል ደጐል በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ብረት ለበስ ተዋጊ መኪና ካላደራጀን ወደፊት የሚነሣብንን የጀርመንን ጦር ልንመልሰው አንችልም ብሎ ከነኛን

ጋር ያቀረበውን አሳብ በሰዓቱ ተቀባይ ሳያገኝ እውነተኛነቱን የተረዱት በዚህ በብረት ለበስ መኪና ጉድለት ምክንያት ሊሸነፉ ሲሉ ወይም ከተሸነፉ በኋላ ነው (1) ።

ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ምንም ቢጥሩና ቢተጉ ጥረቱንና ትጋቱን የእግዚአብሔርና የጊዜ እርዳታ ካልተጨመረበት ማናቸውም ነገር ከታሰበው ግብ እንደማይደርስ ዕውቅ ነው ። የሚቻለውን ሁሉ አድርጎ መሸነፍ በግድ ቢደርስ ጸጸት የለም ። ያዬ ልብነ ድንግል መንግሥት የተቻለውን ሁሉ ያደረገ አይመስልም ። የሆነ ሆኖ ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው ድል ለማድረግም ድል ለመመታትም ለመጠቃትም ለማጥቃትም ተለዋዋጭ ሁኔታ አጋጣሚ ጊዜ በዚህ ዓለም ስለአለ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አብዛኛውን በራሱ ሽፍትነት የተነሣ ተጠቂ ተዘራፊ ተማራኪ ገባሪ የነበረው የአዳልና የሱማሌ ሕዝብ በቅርብ ትንቢትን የተደገፈ ይኸን የወጣት ጀኑመሪ ግራኝን ፤ በሩቅ የኃያሉን የቱርክን ደጋፊነት ስላገኘ የኖረ ጥቃቱን ለመመለስ ቆርጦ በአዲስ ድርጅት በአዲስ ቢጋለ የተበቃይነት መንፈስ ተነሣ ።

በእርግጥ የክርስቲያኖቹን ኃይል የሰበረ የእስላሞቹን ዕድል ያቃናው በተለይ ወደ መጨረሻው የቱርክ መንግሥት በግብፅና በዓረቢያ አገር ግዛቱን ማጽናቱና ከዚሁ ከሰፋው ከቱርክ ግዛት ግማሹ በዘረፋ ሀብትና በወርቅ ለመክበር የቀረውም ቅዱስ ጦርነት (ጂሃድ) የተባለው የሃይማኖት ጉዳይ እያማለለው ለእርዳታ ብዙ የፋርስ ፣ የሕንድ ፣ የዓረብ ፣ የቱርክ ተዋጊዎች ጥሩ ጥሩ መሣሪያ እያመጡ የግራኝን የጦር ኀይል በማጽናታቸው ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለዝምድናና ለእርዳታ ተስፋ የጣሉበት የፖርቱጋል መንግሥት ከኢትዮጵያ ርቀቱ ከ፳ሺ ኪሎ ሜትር በላይ ነው ። መልክተኛ ልኮ መልስ እንኳን ለማግኘት ያምስትና የስድስት ዓመት ጊዜ ማስፈለጉን ፤ እንደዚህም የሚያራዝመው የመርከቡ ጥበቃ የዓረቦቹና የግብጾቹ ቍጥጥር መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ። ስለዚህ እንዶም ሮድሪግ ከአባ ጸጋ ዘአብ ጋር ወደ ፖርቱጋል ከሁለት ዓመት በፊት ተልከው በአሁኑ ሰዓት ያሉበትና የሚያደርጉት በንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ የሚታወቅ አይመስልም ። መልክተኞቹን ከአራት ዓመት በፊት ምጥዋ አድርሶ የተመለሰው ሎፖስ ዲዩጎ ወይም ተከታዩ የሕንድ ጠቅላይ ገዥ ይኸን ግራኝ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ የገመረውን ጦርነት በፍጹም ላይሰማ ይችላል ። ወደቦቹን ምጥዋን ዘይላን ለመያዝ የነበረውም አሳብ በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩን ወደ ፍጻሜ የሚያደርሰው ጠፍቶ ኢትዮጵያ በጠላት ታጥራ ወደቦቿን ፖርቱጋሎቹ ላንድ ጊዜ መጥተው ደብድበው ከተመለሱ በኋላ በአሁን ሰዓት ምጥዋን ቱርኮች ይዘው ዘይላን በቀጥታ የሚጠቀምበት ግራኝና ወገኖቹ ናቸው ።

ስለዚህ የኢትዮጵያና የፖርቱጋል መንግሥታት ቀድሞ ባፄ እስክንድር ጊዜ ከመጣው መልክተኛ ከፔድሮ ደኮሔልሐእ ዠምሮ በተለይ ደግሞ አሁን የቱርክ ኃይልና ሥልጣን በመካከለኛው ምሥራቅ በገነነበት ሰዓት ሁለቱ የክርስቲያን

(1) La France et son Armée.

መንግሥታት የሚያደርጉት የመልክተኛና የገጸ በረከት መለዋወጥ ግራኝ በቱር
ኮች በኩል የሚመኘውን ማናቸውንም ርዳታ ሊያፋጥንለትና በኢትዮጵያ ላይ
የሚያደርገውን ጦርነት ሊያከናውንለት ሲችል ዓፄ ልብነ ድንግልና መንግሥታ
ቸው ግን ለጊዜው ተጐድተውበታል ማለት ነው ። ጦርነቱ ራሱ የተዠመረው የፖ
ርቱጋል መልክተኞች ከኢትዮጵያ በተመለሱበት ዓመት በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ስለሆነ
የወዳጅነቱ ግንኙነት እንዲያውም ጠቡንና ርዳታውን አባብሶታል ማለት ነው ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ግራኝ አህመድ ከአለፈው ጦርነት ወዲህ ሐረር ገብቶ
ትንሽ ጊዜ አርፎ ጦሩን እንደገና ባዲስ መልክ አዘጋጅቶ ከኢትዮጵያ እስካሁን
በዘረፈው ሀብት ብዙ ነገድ አሳብሮ መጥቶ ውጊያውን ሲቀጥል እነሆ እንመለከ
ታለን ። የዚህንም ዝርዝር ታሪክ የሚሰጠን ያው ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ይተር
ከዋል ።

«. . . . . በከተማው (በሐረር ማለቱ ነው) ትንሽ ጊዜ ከቆየ በኋላ ሌላ የጦር
ዝግጅት አደረገ ። ከሀበሻ አገር የተዘረፈውን ምርኮና ዕቃ እየጨመረ ወደ ሱማሌ
ዎችና ወደሌሎችም ነገዶች መላክተኛ ላከ ። ሁሉን ለሚያውቀው ንጉሥ (እግዚአ
ብሔርን ሲል ነው) እንዲታዘዙና ለዚህ ለተቀደሰው ጦርነት እንዲተባበሩ ደብዳ
ቤም ጻፈላቸው ። በደብዳቤውም ውስጥ ተነሡ ጉዟችሁንም ዠምሩ ሀብታችሁንና
ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ ፤ ለእግዚአብሔር ሃይማኖት የሚረዳውን እግ
ዚአብሔር ይረዳዋል የሚል ጥቅስ ከቁራን እየጨመረ ጻፈላቸው ። ወደ ይባሬ
(የበሬ) ነገዶች የተላከው ዓሊ ጕይታ አባቱ በሱልጣን አህመድ ጊዜ ባሊ ላይ የሞ
ተው ሊላው ሁለተኛው መላክተኛ ወደ ጊሪ ነገዶች ባላባታቸው የይማም አህመድ
አማች ወደ ሆነው ወደ ማታን ቢን ኡስማን . . . . . ሦስተኛው መላክተኛ በሃራቡ
በጎይታ ቂዎድርስ ልጅ ውስጥ ለሚተዳደሩ መራይሃን (መሪሃን) ለሚባሉት ነገ
ዶች ነው ። ይማም ለዚህ ለቅዱስ ጦርነትና ለእግዚአብሐር መንገድ ለማሳበር በያ
ለበት ሰበከ ።

የሀበሻ ንጉሥ የናዖድ ልጅ የወናግ ሰገድ ሰዎች ወርቅ ፤ ኡአርስ (የእህል
ወይም ያትክልት ዓይነት) የዝሆን ፤ የአውራሪስ ጥርስ ፤ ጥርኝ ፤ ባሪያ ሌላም ብዙ
ሀብት ወደ አደን ድረስ በባሕር እየተመላለሱ የሚነግዱ ነበሩትና የነርሱን እጉዞ
ላይ መሆን ኤሚሩ ሰምቶ ሁሉንም ቀምቶ ለየነገዱ አከፋፈለውና ለዚህ ጦርነት
ጉዳይ . . . . . ጠቀመ ።

ከዚህ በኋላ ነገዶችም አለቆችም . . . . . ሁሉ የጦር ዝግጅታቸውን ጨርሰው
የጦር መሣሪያቸውን ይዘው እየተከታተሉ መጡልህ የሚሉ ሁለት መላክተኞች
ወደ ይማም መጡ ። በመጀመሪያ ይማም አህመድ ዘንድ የደረሰው ነገድ የሀብር
ማጋጺ ነው ። ባላባታቸው አህመድ ጉራይ ቢን ሁሴን አገዞ ሱማሊ ይባላል ። እነዚ
ህም ነገዶች በሐረር ሸለቆ በላይኛው በኩል በተለይ ቃሻ በሚባለው ሥፍራ ሠፈሩ።
በእነርሱም ውስጥ የፈረሰኛና የእግረኛ ድንቅ የሆኑ የጦር ወታደሮች ነበሩባቸውና
መሣሪያቸውንና ሰልፋቸውን በፈረስ ሆነው አሳምረው አሳዩ ። የነርሱም መም
ጣት ይማም አህመድን በጣም አስደሰተው ። ለነርሱ ይማም መልካም አቀባበልና

ISIC

ክብር አደረገላቸው ። ለአለቃቸው ለአህመድ ጉራኝ የሚያምር ልብስ አልብሶ ሸለመው ።

ቀጥሎ የገራ ነገዶች በባላባታቸው በማታን ቢን ኡስማን እየተመሩ መጡ ። እነርሱም በፈረስ ሆነው መሣሪያቸውን ሰልፋቸውን ለይማም አሳዩ . . . . . ። አለቃቸውም ሚስቱን ፈርጻውሳህ የምትባለውን የይማምን እኅት አስከትሎ መጥቶ ነበር ።

ከዚያ የዘርባ ነገዶች መጡ ። የነርሱም አለቃ የይማም ያባቱ እኅት (ያክስቱ) ልጅ ሱልጣን መሐመድ ይባላል ። ያስከተለውም ጦር አርባ ፈረሰኛ ሺ፣፻ የእግረኛ ወታደር ነበር ። እነርሱንም ይማም በሐረር ሆኖ በታላቅ ክብር ተቀበላቸው ። በእነርሱም ደስ ተሰኝቶ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰገነ ። የጦር ሠራዊቱም ሁሉ በከተማዩቱ (በሐረርጌ) ዙሪያ ሠፈሩ ። አንዱ ሠራተኛ ከሌላው አይገናኝም ነበር ።

ከነዚህ ሁሉ (ከተላከባቸው ውስጥ) ወደ ኋላ የቀረ የስነፈ የማራሂሃን (መራሃን) ነገድ ብቻ ነው ። አለቃቸውም ሂራቡ ጠብና ክርክር የሚወድ ተንኮለኛ ከዳተኛ ነበር ። ይማም ከወታደሮቹ ውስጥ አስከትሎ ወደ ሂራቡና ወደ መራሂሃን ነገድ ሂደና "በምን ምክንያት ነው ወደ ተቀደሰው ጦርነት ለመምጣት የዘገየኸው" ብሎ ቢጠይቀው አለቅየው ችግሩንና ድኅነቱን አመካኝቶ ይቅርታ ጠየቀ ። ይማምም "ጦርነቱን በመከተት ምንም የምትጠቀመው ነገር የለም" ብሎ ይቅርታ አደረገለት ። ከዚህ በኋላ ሂራቡ የወንድሙን ልጅ የበላይ አድርጎ የመራሂሃንን ነገድ ከይማም ጦር ጋር እንዲተባበር ሰጠው ። የነርሱም ቍጥር ፃ ፈረሰኛ ፺፱ የእግረኛ ጦር ነበር ። ሂራቡን ወደኋላው ትቶ ይማም የመራሂሃንን ነገድ ይዞ ወደ ሐረር ተመለሰ ።

ከዚህ በኋላ የሀበሻን አገር ለመውጋት ተዘጋጀ ። የቤቱን ዕቃ ለራሱ አንድም ሳያስቀር የሚስቶቹንም ጌጥ እየሸጠ የጦር መሣሪያ እየገዛ ለየነገዱ ለየወታደሩ አድሎ የጦር ሠራዊቱን አደራጀ ። ለራሱ ምንም ሳያስቀር ይኸን ሁሉ ውጭ ለዚህ ለቅዱስ ጦርነት ማውጣቱ ከአምላኩ የሚያስደስተውን መንግሥተ ሰማያትንና ከሚያማምሩት ቆንጆዎች ዓይናቸው ከጠቋቆረው ሴቶች እንዲቱን ለማግኘትና በጠቅላላው አምላክን ለማስደሰት ብሎ ነው (1) ።

ይኸን ሁሉ ካደረገ በኋላ ጉዞውን በይፋ አስታውቆ ከነጦሩ መንገድ ዠመረ ። የጦር ሠራዊቱም ነገዱም ሁሉ ተቀጣጥሎ በሰልፍ ተከተለው ። የጦርነት አላማም (ሰንደቅ ዓላማም) ተዘረጋ ። ይማም ከሚስቱ ከድል ወበንራ ከኢሚር ማኅፉዝ ልጅ ጋር ይዞንዝ ዠመር ። በዚህም ወራት ድል ወንበራ እርጉዝ ነበረች ። ተጉዘውም ዚፋብ ወደምትባለው ከተማ ደረሱ ። በዚችም ከተማ ሰሲሳይ የሚሆን ብዙ ነገር አገኙ ። በዚያም ከገራድ ዲን የአዳም ልጅ (ያገሩ ባላባት) ጋር ተገናኙ ። እርሱም

(1) በቁራን ውስጥ ዘምድር እግዚአብሔርን ያገለገለ በሰማይ መልካቸው ያማረ ቆንጆዎችን ያገኛል የሚል ጥቅስ ሱራት 44 ቍ 54 ይገኛል ።


ISIC

ደሃ ወዳድ ጻድቅ ነበር ። የነቢዩን (የመሐመድን) ስም ደጋግሞ ማንሣት ይወድ ነበር ። ከርሱም ጋር ሆነው ገራድ ሻሙን (ስምዖን እንደ ኢትዮጵያውያን አጠራር) ገራድ ካሚል የይማም እማች እኅቱን ሙኒሣህን ያገባው ፤ ኤሚር ሙጃሂድ እነዚህ ሁሉ ባንድነት ይማምንና አብሳማ ኑርን (1) በክብር ተቀብለው አስተናገድዋቸው ። ይማም አህመድ ከነጦሩ በዚፋህ ፷ ቀን በሰነበተበት ጊዜ ሚስቱ ድል ወንበራ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙም መሐመድ ተባለ ። ስለዚህም ድል ወንበራ ወደ ኋላ ከግራኝ እኅት ከሙኒሣህ ዘንድ ቀርታ ነበር ። እስላሞቹ ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው ውኃ እሞላበት ኤዲር እሚባለው ሥፍራ ደረሱ ። በዚያም ትንሹም ትልቁም ወደ ሠግኖቹ እየመጣ ተደባለቀ ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ያበሻ ንጉሥ ወናግ ሰገድ ባደቁ እሚባል አገር ላይ ሳለ እስላሞች አገርህን እየዘረፉ አብያተ ክርስቲያናትህን እያቃጠሉ ወደፊት ይገሠግሣሉ ጦራቸውም ብዙ ነው የሚል ወሬ ነጋሪ መጣለት ። ይኸን ሲሰማ ቤተ ሰቡን መኳንንቱን ሹማምንቱን አስከትሎ የግዛቱ እማካይ ሥፍራ ወደ ሆነው ወደ ቤተ አምሐራ ሄደ ። ይኸም አገር ለርሱም ላባቶቹና ለቅድም አያቶቹ መኖሪያና መደበኛ ሥፍራቸው ነው ። ለባደቁ አገር (ጥቢታ) እስማን ቤን ዳር ዓሊን (አውራይ እስማን) ትቶት ሄዶ ነበር ። ይኸም ሹም በሱልጣን መሐመድ ጊዜ ከናባቱ ተማርኮ ሄዶ ሃይማኖቱን ለውጦ ክርስቲያን ሆኖ ይኖር ነበር በኋላ ግን ተጸጽቶ ተመልሷል ።

ንጉሡ ወናግ ሰገድ ቤተ አምሐራ ሆኖ ብዙ ሠራዊቱን ሰበሰበ ። የትግሬ ፤ የአንጎት ፤ የጐጃም ፤ የቤጌምድር ፤ የአንጎት ፤ የቅዳ ፤ የጋኝ ክርስቲያንና የባሕር ዳር ሕዝብ ሁሉ በዙሪያው ተሰበሰበ ። የትግሬ የታወቁት መኳንንቶች ብቻ ቍጥራቸው ፷፬ ይደርሳል ። እያንዳንዱ መኰንን በውስጡ የሚታዘዘው ጦር ነበረው ። እንደዚሁም የቤጌምድሩ የአንጎቱ የቅዳው የጋኙ ብዛታቸው እንደ አንበጣ ስለሚመስል ከእግዚአብሔር በቀር ሊቆጥራቸው የሚችል አልነበረም ። የክርስቲያኖቹ ወታደሮች መሣሪያቸውን ይዘው እንደ ተዘጋጁ በያለቃቸው በየደረጃቸው ሆነው በቤተ አምሐራ ተሰብስበው ነበር ። አባስ የሚባል ሃይማኖቱን ለውጦ ክርስቲያን ሆኖ የነበረ በኋላ የተመለሰው ያን ጊዜ በቤተ አምሐራ ከንጉሡ ዘንድ ነበርና የነገረኝን አስታውሳለሁ (ያረብ ፋቂህ ቃል) እርሱንም ንጉሡ እንደዚህ ብሎ ጠየቀው "አባስ ምን ይመስልሃል ጦር ሠራዊታችንን ይማም ሲያይ የሚዋጋ ይመስልሃል ወይስ አይመስልህም" የአባስ መልስ "እርሱ ከሁለት አንዳቸው መልክም መስሎ የታየውን መያዙ አይቀርም ፤ ጦሩ ግን የሚያደርገውን አላውቅም" ንጉሡ "እውነት አለህ ጦሩ ይመክታል ብትለኝ ኖሮ እንደ ውሸታም እቆጥርህ ነበር ባንተም

(1) የግዕዙ ዜና መዋዕል አባ እስማን ኑር ይለዋል ፤ ታሪክ ነገሥት . . ባሴት ሬኔ ገጽ 333



በቅርብ ጊዜ ከቱሉ ዲምቱ የተገኘው የጽላት ቅርጽ በዚህ በባደቁ ጦርነት የፈረሰ ወይም ያንጊዜ የተ
ደበቀ ሳይሆን አይቀርም ።

ምንት አይኖረኝም ነበር አንተ ግን አላውቅም ማለትህ ደግ አደረግህ" (1)» ሲል ዓረብ ፋቂህ የዚህን ጉዳይ እዚህ ላይ ያቆማል (2) ።

እንደ ዓረብ ፋቂህ አነጋገር ግራኝ አህመድ መገሥገሪያ ከራስ ደገልሃን ቀጥሎ ከአርባ ሺ.መልና ከገምግናው ከወናግ ገሮን ጋር ከተዋጋ በኋላ ሐረር ተመልሶ ከኢትዮጵያ በዘረፋ ያገኘውን የምርኮ ሀብት ለየባላባቱ በማደልና በመሰበክ ከቆየ በኋላ ያሁኑ አመጣጥ ከፍ ባለ ዝግጅት መሆኑን ጽሑፉ ያመለክታል ። ግራኝ ወደ ሐረር ተመልሶ በሚዘጋጅበት ጊዜ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ባደቂ ነበሩ ። ከዚህ በፊት እንዳልነው ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን ከሥልጣኔ የራቀችበት ጊዜ በመሆኑ ነገሥታቱ ቤተ መንግሥትና ከተማቸውን በእንጨትና በተራ ግንብ እንጂ በጥሩ ሕንፃ ስላልሠሩ ይህ ባደቂ እያለ ዓረብ ፋቂህ ደጋግሞ የሚጠራው ከተማ ዛሬ በት ክክል ወዴት መሆኑ አይታወቅም ። መቼም ጸሐፊው በዚሁ ከተማ አጠገብ የሞጀ ወንዝ አለ ብሎ ስለሚጠቅስ ላፄ ልብነ ድንግል ከቀድሞ ከተማቸው ከየረር ከበ ካን በቀር ሌላ የጠፋ ያን ጊዜ ባደቂ የሚባል ትልቅ ከተማ በሞጀ አጠገብ ነበራ ቸው ማለት ነው ። ምናልባት በቱሉ ዲምቱ ውስጥ ቴዎድሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የደንጊያ ቅርጽ ከተገኘበት ላይ ሊሆን ይችላል ።

ስለዚህ ዓፄ ልብነ ድንግል በዚህ በከተማቸው ሳሉ የጦር አለቆቻቸውን አሟ ሟት የግራኝን የጦርነት አያያዝ ከአመዛዘኑ በኋላ በተለይም አሁን ግራኝ ወደ ሐረር ሄዶ ነገዱን ሁሉ አሳድሞ አዳዲስ ጦር ከመመልISTC ላይ ይገኛል የሚሉ ወሬ ሲሰሙ ባደቂን ትተው ወደቤተ አምሐራ ሄደው በበኩላቸው ጦር ያዘጋጁ እንደነበረ ዓረብ ፋቂህ ያመለከተው ትክክል መሆን አለበት ።

የግራኝንም የጦር ምልመላውንና ነገዱን ሁሉ በየአገሩ እየላከ መቀስቀሱን በሰፊው በዘረዘረበት ላይ ግራኝ የራሱን የግል የቤት ዕቃውን የሚሰቶቹን ጌጣ ጌጥ ሳይቀር እየሸጠ አዳዲስ መሣሪያ በመግዛት የተገዛውን ለወታደሩ እያደለ ቅዱስ ጦርነት ብሎ ላመነበት ጉዳይ ማዋሉን ተዘጋጅቶም ሲጨርስ ለጦርነቱ ወደ ባደቂ መመለሱን ። ያቺም ኃይለኛ ሚስቱ ቀኗ የደረሰ ነፍሰ ጡር ሆና እንኳን እስከትወ ልድ ድረስ ሐረርጌ ለመቆየት ትዕግሥት አጥታ ተዋጊውን ባሏንና ዘማቹን ጦር ለማበረታታት ስትል አብራ ተጉዛ ዚፋህ እተባለው አገር ድረስ መጥታ በመው ለዷ ምክንያት ብቻ እዚያው ዚፋህ ከተባለው አገር ከግራኝ እኅት ከሙኒሣህ ጋር መቆየቷን ያመለክተናል ።

ታሪክ ነገሥቱ በግራኝም ባፄ ልብነ ድንግልም በኩል የተደረገውን ድርጅት ራሱንም ወደፊት የምናነበውን የባደቂን ጦርነት በፍጹም አያነሣውም ። ስለዚህ ዓረብ ፋቂህ የራሱን ወገን እያየ የኛን ወገን ወሬ እየጠየቀ ባለፈው ያነበብነውን የታሪክ ቅርስ ስለተወልን በርሱው ጽሑፍ መሠረት የሁለቱን ጦር መሳለፍ ካነበ ብን በኋላ አሁን ወደ ጦርነቱ እንገባለን ።

(1) እንደሙሴ ባሴት ሬኔ ረዚ የሚባለው ጣሊያን የተረጐመው ከዚህ ለየት ይላል "ይማም ይኸን ጦር ሲያይ ይመከታል ወይስ ይሸሻል ቢሉት ይማም ከዚህ በላይ አሥር እጥፍ ጦር ቢያይም መግጠሙን አይተውም አላቸው ።" ንጉሡም እውነት ተናገርህ ጉሽ አሉት ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 65 - 82

# ምዕራፍ ፴፰

## የግራኝ አህመድ ጦር በሰልፍ ወደ ባደቄ ስለመጓዙ

ግራኝ አህመድ ከሐረርጌ ጦር አዘጋጅቶ ኤዲር ከደረሰ በኋላ አሁን ወደ ባደቄ ያደ ረገውን ጉዞ ዓረብ ፋቂህ በዝርዝር እንደዚህ ሲል ጽፎታል «እስላሞቹ ኤዲር ላይ ተሰብስበው ሳለ ከዚያ ሁለት ቀን ተጉዘው በቁልዛር (1) ከሚባለው ውኃ ከሞላ በት ሥፍራ በደረሰ ጊዜ ጦሩን ለውጊያ ማሰለፍ ገ[ሮ]መረ ።

፩ኛ. ለወዚር አዶሌ በውስጡ የሲምን ሕዝብ የአህመድ ጉራይንና የሀብር - ማጋ ዲን የሱማሌ ነገዶች ጨምሮ የሚዘምትበት ነጭ ሰንደቅ ዓላማ ሰጠው ። ከርሱ ጋር ፪፻ ፈረሰኛ ፪ሺ የእግረኛ ጦር ነበር ። የፈረሰኛው ወታደር አለቆች መለሳይ (2) ነበሩ ። እነሱም ኤሚር ሙጃሂድ ሱሀ ፣ አብሳማ ኑር ፣ ገራድ ሻሙን . . . . . ገራድ ኤል ዋራዲ ነበሩ . . . . . . ። ይህ የመጨረሻው መን ገድ መሪና የታወቀ የፈረሰኛ ገ[ር]ግና ነበር ። እነዚህ ሁሉ ይህን ጦርነት ለማድ ረግ ከልባቸው ቆርጠው የተነሡ ነበሩ . . . . ከነርሱም ጋር ፍጹም ጉታ ስለ ሃይማኖቱ የሚሞተው ዋሸራ ሼክ ሐም እነዚህን ፈረሰኞች ከሚከተሉት ጻድቃን ውስጥ አብሮ ነበር ።

፪ኛ. ለሱማሌዎች አለቃ ለኡስማን ቤን ካሌድ ልጅ ለአማቹ ለማታን በውስጡ ፩፻፲ ፈረሰኛ ፫ሺ የእግረኛ ጦር አድርጎ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሰጠው ። እርሱም የጉበሀች ጉበዝ ስለ[illegible] የሀብርን ፣ የጊሪን ፣ የማዝራን ሱማሌ ሁሉ በው ስጡ እንዲያገዘ ጨመረለት ።

፫ኛ. ለወዚር ኑር ቤን ኢብራሂም በውስጡ የሸዋን (3) በይማም ወንድም በመሐ መድ ቤን ኢብራሂም የሚመሩትን የሀርጋይን ነገዶች በሱልጣን ኡመር ዲን ወንድም የሚታዘዙትን የጀራርን ሰዎች አድርጎ ቀይና ብጫ የተደባለቀበትን ሰንደቅ ዓላማ ሰጠው ። የነርሱም ቍጥራቸው ፩፻ ፈረሰኛ ፪ሺ እግረኛ ነበር ። በርሱ ውስጥ የሚታዘዙት የታወቁት ፈረሰኞች ሼክ ዳውድ ፣ ሼክ ዘማላህ ፣ ገራድ ዓሊ ፈንጋላህ ፣ ጎይታ ኢብራሂም የገዳይ (አገር) ጉታ ፣ ፋራቃሃም ወስ ንጊ ፣ ጎይታ ኡስማን ነበሩ ።

የይማም አህመድ ሰንደቅ ዓላማ ደግሞ ዳር ዳሩን በቀይ ተከፍፎ መካከሉ ነጭ ነበር ። ዳር ዳሩን በቀዩ ክፈፍ ላይ "በእግዚአብሔር ስም መሐሪና ይቅር ባይ ላንተ ሰንል ያማረ ድል አድራጊነትን አመጣንልህ ። በዚህ ያለፈና የዛሬውን ኃጢ

(1) በቁልዛር ቀድሞ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ደራደርን የወጋበት አገር ነው ። የአምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ገዞል ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 284 ። በዚያ ላይ በቁልዛር ወይም ብቁል ዘር ተብሏል ፣ ቍጥር 4 ፣

(2) መለሳይ የግራኝ ዘር ያለበት የጠቅላላ የነገድ ስም ስለሆነ ከዚህ ነገድ የሚወለዱትን ሹማምንት ሁሉ መለሳይ ይላቸዋል ዓረብ ፋቂህ ገጽ 111 - 112

(3) አዋሽ አጠገብ ያለውን እስላሞች ያሉበትን እንጂ ዛሬ ሸዋ የሚባለውን አገር አይመስልም ።

ለትህን ይቅር እንዲልህ ደገኛ ሥራውን እንዲያድልህ ወደ ቀጥተኛው መንገድ እን ደምራህ . . . . .” የሚል ጥቅስ ተጽፎበት (ተጠልፎበት) ነበር ። በመካከሉም አራት መሥመር ተከታትሎ “እረፍት አድርጉ ለጸሎት ተዘጋጁ ምጽዋት ስጡ . . . . .” በአንደኛው “በሕያው በዘለዓለማዊው አጸናሁዋችሁ በማይሞተው ሕማ ምን ከራሳችሁ ላይ አስወገድሁ . . . . .” በሁለተኛው “ሌላዩቱ ሕይወት (መንግ ሥተ ሰማያትን) እግዚአብሔርን ለሚፈራ ትገባዋለች ፣ የአዳም የሁለቱን ልጆቹን መሥዋዕት ባቀረቡ ጊዜ የሆነውን እውነተኛ ታሪክ ተረክላቸው” የሚል በሦስተ ኛው “ጦርነት የጀመርህ እንደሆን ስንፍናን አታግባ በሽብር ጊዜ ጽና ሞት በዕድል ካልሆነ በቀር አይደርስም” የሚል ባራተኛው መሥመር ተጽፎ ነበር ።

እነዚህን ጽሑፎች ያዘጋጀው ቅዱስ ሕግና ሥርዓት አዋቂው የእስላሞቹ ሙፍቲ ሲድ አቡበከር የናስር ኤዲን ልጅ . . . . . ነው ። እርሱም በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ከይማም አህመድ አልተለየም ። በሌሎቹም ጦርነት ጊዜ ነበር ። ሲሄድም ተቀምጦም ቆሞም እፈረሱም ላይ ሆኖ ቁራንን ከመድገም አያቋርጥም ነበር ። ለእ ስላሞችም ሁሉ ሰባኪና መምህር ነበር ። ቁራንን በሚደግምበት ጊዜ ሁሉ ስለጦር ነት የሚናገረውን ክፍል እየጠቀሰ በመናገር ለጦርነት እየቀሰቀሰ እስላሞቹን ሁሉ ውጊያ እንዲያምራቸው ያደርግ ነበር ።

የእስላሞቹ ይማም አህመድ ቤን ኢብራሂም (ግራኝ) በመካከል ሆኖ በዙሪ ያው ፱፻ ፈረሰኞችና አሽከሮች ፣ የተሜኑ ፈረሶችን አስከቱ[illegible]ጓዝ ነበር ። ከስመ ጥሩዎቹ ፈረሰኞች ውስጥ ሁሴን ኢል ጋቱሬ . . . . . ከዚህ በፊት ክርስቲያኖቹ ማር ከው በኋላ አምልጦ የመጣው ፣ ኢሚር ዘሀርቡይ መሐመድ . . . . . ኩሽም አቡበ ከር . . . . . ገራድ አህሙሹ . . . . . ገራድ አብድ ኢን ናስር . . . . . . ክርስቲያኖ ችን ሲያይ ካልተያዘ በቀር የማይቆመው እልሁ ከመገንፈሉ የተነሣ ካፍንጫው ደም የሚንቆረቆረው ለጦርነት ታላቅ የፍቅር ሕመም ያለው ሳብር ኤድ ዲን . . . . አብረው አሉ ።

በዚህ ዓይነት ዓረብ ፋቂህ የጦሩን አሰላለፍ የተዋጊውን የእግረኛና የፈረ ሰኛ ወታደር ቍጥር ከመሪዎቹ ስም ጋር ጦር የጠማቸውን በገዮግንነት ስመ ጥሩ የሆኑትን የፈረሰኞች ስም እየጠራ ጦርነቱ የሚደረግበትን ከፍተኛ ዓላማ ጭምር በሰፊው ያሳየናል ። የእግረኛውን የፈረሰኛውን ጦር ልብ የሚነካውን ለጦርነት የተዋጊውን መንፈስ የሚቀሰቅሰውን ክፍል ከቁራን ውስጥ እየመረጡ በየአንዳ ንዱ የዘማች ባንዲራ ላይ በጥልፍ እየተጻፈ ሕዝቡ እንዲያነበው የሚያደርጉ ለሕዝ ቡም በቀጥታ ከዚሁ ከቁራን እያወጡ ከራሳቸውም እየጨመሩ ሕዝቡን በመንፈ ሳዊ አባትነት በስብከት የሚያበረታቱ እነሲዲ አቡበከር እንደነበሩ ከጥቅሱ ዓይ ነት ጋር ያሳያል (1) ።

(1) በባንዲራው ላይ የተጠቀሱት ቃሎች በቁራን ውስጥ የሚገኙበትን ምዕራፍና ቍጥር የዓረብ ፋቂ ህ መጽሐፍ ወደፈረንሳዊ የተረጐሙት ባሴት ሬኔ ከዚህ እንደሚከተለው ዘርዝረውታል ሱራት ቍጥር 171 173 ሱራት ቍጥር 251 ሱራት ቍጥር 123 ። ሱራት ቍጥር 247 ። ሱራት ቍጥር 177 ቍጥር 177 ሱራት ቍጥር 79 ገጽ 115 - 125 ፤

የዛሬ ዘመን ተዋጊ ሕዝብ በሠለጠኑት አገሮች ተዋጊው ወታደር ያገኘ ፍቅር ከተማሪ ቤት ገርምሮ ሲማረው የኖረ በመሆኑ ጦርነት በተደረገ ቍጥር ስላገርህ ስለ ወገንህ በዠግንነት ተዋግተህ ሙት ተብሎ እምብዛም አይሰበክለትም ። ከጠላትህ ጋር ስትዋጋ ብትሞትም ነፍስህ መንግሥተ ሰማያት ትገባለች ብሎ መስበክ በሠለጠኑት አገሮች ችላ ተብሏል ። እርግጥ አንዱ ክርስቲያናዊ ወታደር በጦርነት ከፋኝ ቆስሎ ከሞት አፋፍ ላይ ያለውን ወታደር እናዘው የፍትሐት ሥነ ሥርዓት የሚ ፈጽሙ የካህናት ወታደሮች በጦር ሠራዊት ውስጥ ይገኛሉ ።

በዚህ በመካከለኛው ዘመን ግን በእኛም ዘንድ የክርስቶስ ፍቅር በእስላሞቹም ዘንድ የመሐመድ ፍቅር ትኩስ ነው ። የሁለቱም ተዋጊ ሕዝብ መንግሥተ ሰማያትን በመፈለግ ረገድ ያላቸው አስተያየትና ፍላጐት ተመሳሳይ ነው ። በዚህ በኩል ከወንጌል በነዚያ በኩል ከቁራን መጠቀሱ የተለመደ ነው ። ፪ቱም ወገኖች አምላክን ይለምናሉ ። አሸናፊውን ግን እግዚአብሔር ያውቃል ።

ስለዚህ ግራኝ ይኸን ለውጊያ የተከተለውን የአዳል ፤ የኢሳ ፤ የሱማሌ ፤ የዓረብ ልዩ ልዩ ነገድ የውጊያ መንፈሱ እንዲግል በክርስቲያኖች ላይ ያላቸው ጥላቻና በቀል በፍጹም እንዳይቀዘቅዝ ራሱም እየሰበከ እንደበታቸው የረታውን በተዋጊው ሠራዊት ዘንድ የተከበሩትን ሼኮች አስከትሎ ያሰብክ ነበር ማለት ነው ። ከውጊያ በፊት የተዋጊን መንፈስ በዚህ ዓይነት በቅድሚያ ማዘጋጀት የድል መድን መሆኑ በዛሬም ጊዜ ቢሆን የታመነበት ነው ። ጦርነቱ የግድ በመሆን ፈንታ የፈቃድ ሲሆን የድል ፍሬ እንደሚሰጥ የታወቀ ነው ። ለቅዱስ ጦርነት መሞት መንግሥተ ሰማያትን ያስገኛል ተብሎ ሲሰበክ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ተስፋ ለሚያደርገው ሁሉ ጉልበትና ጽናት እንደሚሰጠው ግልጽ ነው ።

በኛ በኩል የጦርነቱ ታሪክ ራሱ ስለአልተጻፈ ግብፃዊው ጳጳሳችን ያገር ተወላጆቹ የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖች እጨጌው ንቡረ እዱ ዓቃቤ ሰዓቱ ቄስ ሐፄው በጠቅላላው ቀሳውስቱ በዚህ በጦርነት ሰዓት በስብከታቸው ፤ በንግግራቸውና በመንፈሳዊ አባትነታቸው ተዋጊውን እስከምን ድረስ እንዳጸኑት መጠኑን ለመገመት ይቸግረናል ። ግራኝና ዋናው ሼክ ሲዲ አቡበክር እንዳደረጉት በሰንደቅ ዓላማ ላይ ከብሉይና ከሐዲስ የጦርነት ጥቅስ እያወጡ መጻፍ አለመጻፋቸውን እናውቅም እንጂ "ስለሃይማኖቱ እየተዋጋ የሚሞት ሰማዕትነት ያገኛል" ብለው እየተዋጋ የሚሞተውንም "እግዚአብሔር ይፍታ" እያሉ የሚያናዝዙ ይኖሩ ይሆናል ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ግራኝ አህመድ በባደቄም ይሁን ወደፊት በሚደረገው በታላቁ የሽምብራ ኩሬ ጦርነትም ያሸንፋል የሚሉ ጥርጣሬና ሥጋት ያለ አይመስልም ። ከሌለም ወታደሩን በመንፈሳዊ አነጋገር እስከ መስበክ የሚያስጨንቅ ነገር የለም ብለው ሁኔታውን በቸልታ ሳያልፉት የቀረ አይመስልም ። ደንበኛ ሥጋት የደረሰው ከሽምብራ ኩሬ መሸነፍ በኋላ ነው ። ጸሎትና ምህላ ዋይታና ለቅሶም የተከተለው ከዚሁ ጦርነት በኋላ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከነሠራዊቱ ከሐረርጌ እየተጓዘ አዋሽን ተሻግሮ በፊቱ ያገኘውን እየዘረፈና ስንቅ እያዘጋጀ አማጃህ ወደ ምትባል የንጉሡ ከተማ

ደረሰ ። ይህቺም ከተማ በዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ከከሰምና ከዱከም ወንዝ የማትርቅ በውስጧ ብዙ የእስላም ነጋዴዎች ያሉባት ናት ። በዚያ ሳለ ግራኝ ስለንጉሡና ስለ ጦራቸው እየተጠያየቀ ወደ ባደቄ መቅረቡን ለማስረዳት ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ታሪኩን ይቀጥላል ።

«ከዚያ ይማም ሌሎቹም በአማጀህ ተሰበሰቡ ይህቺም አገር የሀበሻ ንጉሥ ከተማ ናት ። በውስጧ ግን እስላሞች አሉ ። የከተማው ነዋሪዎች ወደ ይማም መጡና "ያበሻ ንጉሥ ጉልቆ መሳፍርት የሌለው ጦር አለው ። ፈረሰኛውን እግረኛውን .... ከእግዚአብሔር በቀር ቆጥሮ የሚያደርሰው የለም ። አባቶችህም አያት ቅድም አያቶችህም አማችህ ኤሚር ማኅፉዝም ፤ ኤሚር ዓሊም የሳዓድ ዲን አገር የጥንት ሱልጣኖችም እስካሁን ድረስ ያበሻውን ንጉሥ አገሩና እቤቱ ድረስ መጥቶ ሊወጋው የደፈረ የለም ። እነዚህ ሁሉ ባገራቸው ወሰን ላይ አንድ ጊዜ ወረራ አድርገው ምርኮ ዘርፈው ይመለሳሉ ። ከክርስቲያኖቹ ውስጥ አንዱ የተከታተላቸው እንደ ሆነ የያዙትን እንዳይነጠቁ ይከላከላሉ ። አንተ ግን እዚሁ አገር ድረስ መጥተህ ያበሻን ንጉሥ ልትወጋው ደፍረሃልና የእስላሞች ፍጻሜ እንዳይሆን ተጠንቀቅ" አሉት ። ይማም መልሶ "በእግዚአብሔር መንገድ ቅዱስ ጦርነት ማድረግ ለኛ ለእስላሞቹ ከባድ አይደለም ። እኛ ምኞታችን ይህን የተቀደሰ ጦርነት መዋጋት ነው ። ከኛ መካከል የሚሞት ቢኖር መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል ። በሕይወት የሚኖረው በደስታ ይኖራል ። ወናግ ሰገድ ቍጥሩ የበዛ ጦር እንዳለው እናውቃለን ። እኛም ጦሩን በጦር ኃይሉን በኃይል ተዋግተን እግዚአብሔር ላከበራት ለዚች ሃይማኖት መጋደል እንፈልጋለን" አላቸው ። በዚያን ጊዜ የአማጀህ ሰዎች አለቀሱ ። የቁራንም ግልባጭ በራሳቸው ይዘው እስላሞቹን ሁሉ አክብረው አስተናገዱና ድል አድራጊነትም እንዲያገኙ ተሳሉላቸው ።

ባራተኛው ቀን በድሆህር (1) ጸሎት ጊዜ እስላሞቹ ጉዞ አድርገው ዣን ዘላቅ እሚባል ሥፍራ ደረሱ ። በዚያም ከሰም የሚባል ተራራ ነበር በርሱም ላይ ክርስቲያኖቹ እንዳሉበት ተመለከቱ ። ከዚህ በኋላ ይማም አህመድ ፴ ፈረሰኞች መርጦ ወደ ተራራው አጠገብ ሄደ ። ከተራራውም ላይ አራት የክርስቲያን አለቆች ፬ ፈረሶች እግረኞችም ጨምረው ወረዱ ከነርሱም ውስጥ ናስር (በኋላ ወደ ግራኝ ገብቶ ያገለገለ) ነበር ። እስላሞቹ ጠብቀው እነዚያ ሲመጡ ተዋጉዋቸው ። ጦርነቱን የገፋው ሙሐመድ ቢን አድሩህ ነው ። እርሱም አንዱን የክርስቲያን ፈረሰኛ ወግቶ ጣለው ። ካሌድ አል ዋራዲም እንደዚሁ አደረገና እስላሞቹ አሸነፉ ፤ ክርስቲያኖቹ ሸሹ ..... ። እስላሞች ፲፪ ፈረሶችና በቅሎም ሁንጋም ማርከው ይህ የድል መዥገሪያችን ነው ብለው ወደ ሠፈር ተመለሱ ። በሠፈርም እሳት እያነደዱ ግማሹ ቁራን ሲደግም ግማሹ እግዚአብሔርን የቀረው ነቢዩን ሲያነሣ ይማም አህመድ ብዙ ክርስቲያኖች ማርኮ ነበርና ስለሀበሻው ንጉሥና ስለጦሩ ቢጠይቃቸው እንደዚህ ብለው መለሱለት "አውራይ ኡስማን ቢን ዳር ዓሊ ብዙ ጦር ይዞ ከዚህ እና

(1) ድሆህር የእኩለ ቀን ጸሎት ።

ISIC

ንተ ካላችሁበት በማይርቅ ዱከም በሚባለው ወንዝ አጠገብ ይገኛል ..... ። የት ንጉሡ ወናግ ሰገድ ግን ጦር ሠራዊታቸውን ይዘው በቤተ አምሐራ ናቸው ። የት ግሬ ጦር ሠራዊትም መጥቶ ደብረ ብርሃን (የተጉለት) ነው ያለው አለቅዬውም ተክለ ኢየሱስ ይባላል ። በርሱም ውስጥ ሌሎች ሹማምንት አሉ ከነዚሁም ውስጥ ፍቅረ ኢየሱስ ፡ ዋሹ (ጐሹ ?) ኡስማን ናቸው» (1) ።

ዓረብ ፋቂህ የግራኝን አመጣጥ በዚህ ዓይነት ይተርካል ። ይህ በውስጡ እስላ ሞች የሚገኙበት አማጃህ የሚባለው ከተማ ወይት እንደሚገኝ ከተማነቱም ቢቀር ዛሬ በዚህ ስም የሚጠራ መንደርና ቀበሌ በዚህ በየረርና በዱከም ወይም በቡልጋ አቅራቢያ መኖር አለመኖሩን አላረጋግጥም ። እንግዲህ ግራኝ ከነጦር ሠራዊቱ ወደዚች አገር ሲገባ ከክርስቲያኖቹ ውስጥ የፈሩት ቀደም ብለው ወይነ ቢትወደድ ሠርፄ ዘንድ መሸሻቸው የታወቀ ነው ። አንዳንዶቹም በውግያም ያለውግያም የተ ማረኩ አሉ ። ግራኝ የንጉሡንና የጦራቸውን ሁኔታ ለመረዳት የፈለገው ከነዚህ ነው ማለት ነው ።

እስላሞቹ ግን ምንም በዜግነት የንጉሡ ነገሥቱ ቢሆኑ በሃይማኖት ከዲሱ ወራሪ ጋር አንድ ስለሆኑ ሳይሸሹ ተቀብለውታል ። በሚያውቁት መጠን ቍጥር የሌለውን የንጉሡን ሠራዊት ከአባቶችህ ማንም ያላደረገውን ለመውጋት ደፍረህ መጥተሃልና ተመለስ ብለው ልባዊ ምክር አቅርበዋል ። የወናግ ሰገድን የሠራዊት ብዛት አውቃለሁ ነገር ግን ልንወጋው ቆርጠናል ከመካከላችን የሚሞት በኖር መንግሥተ ሰማያት ይገባል ። የሚተርፈው በደስታ ይኖራል ብሎ ቁርጠኛ ቃል በነገራቸው ጊዜ ቁራን በራሳቸው ላይ ደፍተው ከማልቀስ ጋር ድሉ እንዲቀናው ተሰለው አሰናብተውታል ። እንግዲህ ከዚህ ሁሉ በኋላ በማረካቸው ክርስቲያኖች እየተመራ የባደቄ ከተማ ወደሚገኝበት ወደ ዱከም ወንዝ አጠገብ መጥቶ ከሽም ብራ ኩሬ በፊት የተዋጋበት የባደቄ ጦርነት በሚቀጥለው ምዕራፍ ይነበባል ።

## ምዕራፍ ፴፮

### የባደቄ ጦርነትና ጦርነቱን የተካፈሉት የኢትዮጵያ መኳንንት ቢትወደድ ሠርፄ ፡ ሕዱግ ራስ ማኅፀንቶ ፡ አውራይ ኡስማን ፡ ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ፡ ጸሐፊ ላሕም ሮቤል (፲፭፻፳፩ ዓ. ም. መስከረም)

በዚህ ምዕራፍ የተደረገውን ጦርነት የተካፈሉትን በዚህ ምዕራፍ እርእስት የሚነበ ቡትን ዓረብ ፋቂህ ያምስት ታላላቅ መኳንንት ስም ጠቅሷል ። ከነዚሁ የመጀመሪ ያውን ቢትወደድ ሠርፄን ከማዕርግ ስሙ ጋር በትክክል ሲጠቅስ አውራይ ኡስማ ንን ያለ ማዕርግ ማኅፀንቶንና ተክለ ኢየሱስን ሮቤልን አዝማች የሚል የማዕርግ ስም ሰጥቷቸዋል ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 92 - 96

በዚህ ዘመን ያለውን የሹመት ዓይነት ስናነብ ለአብዛኛው የቀኝና የግራ እየ ተባለ ሹመት በጥንድ ሲሰጥ እናገኛለን ። በአሁን ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል በአንድ ሚስት ተወስነው እስኪሹሩት ድረስ በቀድሞ ጊዜ የንገሥታቱ ሕጋዊ ሚስቶች የግራ ባለቤት (ግራ ባልቴሐት አንድ አንድ ጊዜ በዓልቲሐት ሌላ ጊዜ ደግሞ በዓ ልተ ቤሐት) እና የቀኝ ባለቤት ይባሉ ነበር (1) ። በዚሁ ዓይነት የግራ ቢትወደድ የቀኝ ቢትወደድ ፥ የቀኝ አዛዥ የግራ አዛዥ ፥ የቀኝ ጸሐፌ ትእዛዝ የግራ ጸሐፌ ትእዛዝ ፥ የግራ ሕዱግ ራስ የቀኝ ሕዱግ ራስ ይባሉ ነበር (2) ።

ስለዚህ በአርእስቱ ስሙ የተጠቀሰው ቢትወደድ ሠርፄ የግራ ቢትወ ደድ በነበረበት ጊዜ ይስሐቅ የሚባል ቀኝ ቢትወደድ ነበር ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሠርፄ እንደዚሁ የግራ ቢትወደድ ሳለ በድሌ (በድላይ) የቀኝ ቢትወደድ ነበር ። ማኅፀ ንቶ አንድ አንድ ጊዜ መጽሐፉ እምሐ ጥንት ይለዋል ። እርሱም በታሪከ ነገሥቱ ውስጥ ሕዱግ ራስ ማኅፀንቶ ተብሎ ይገኛል (3) የቀኝ ወይም የግራ መሆኑን አይለ ይም ። አልቫሬጽ በመጽሐፉ ሕዱግ ራስ የሚባል የማዕርግ ስም ያለው ባለሥል ጣን ባልደረባ ተሰጥቶን ነበር የሚለው ማኅፀንቶን ይሁን ወይም ሌላ አይታወ ቅም (4) ።

አውራይ ኡስማን ግን ቀድሞ እስላም አሁን ግን ክርስትና ተነሥቶ ዋና ባለ ሥልጣን የነበረ ስለሆን አውራይ የሚባለው ሥያሜ በኛ "ልጅ" ልጅ እገሌ እንደ ሚባለው እንደ ማዕርግ ስም ስለሚቆጠር በዚሁ የረጋ ይመስላል (5) ።

ዓረብ ፋቂህ የሠርፄን ቢትወደድነት ሲጠቅስ[illegible]ፉትን ማኅፀንቶን ተክለ ኢየሱስንና ሮቢልን "ፓትሪስ - አዝማች" ነው የሚላቸው ። ይህ ስያሜ ከትልቁ ቆስጠንጢኖስ ዝምሮ ከውጭ አገር ሸሽተው በተለይ የሮማን ቄሣር መጥተው ለተ ግጠኑ መሳፍንትና መኳንንት የሚሰጥ የማዕርግ ስም ነበር ። ትርጉሙ PATER አባት ከሚለው ከላቲኑ የመጣ ሆኖ በላቲን PATRICIUS ይባላል (6) ። በፈረን ሣዊPATRICEስለሚል የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ የተረጐሙት ረኔ ባሴት በዚሁ ቃል ነው ። ለዚህ ቃል በአማርኛ የሚቀርበው አባት ወይም የበላይ አዝማች ከማ ለት ይልቅ እንደዚሁ አዝማች ማለት ነው ።

ስለዚህ ፈረንጆችና ዓረቦች ትክክለኛውን የማዕርግ ስም ሊጨብጡት ያልቻ ሉትን የኛን ሹማምንት ሁሉ በደፈናው "ፓትሪስ - እገሌ" እያሉ መጥራት ስለ

(1) የኢ.ት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 29

(2) Liber Axume-K. Conti Rossini (Secretariat du Corpusco. Lauvain. Reimpression Anastatique 1962. ገጽ 36 - 41

(3) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92

(4) አልቫሬጽ . . . . ምዕ. 69

(5) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 10 ቍጥር 2 የረኔ ባሴት ማስታወሻ

(6) Littré ገጽ 1559

እስለመዱ በዚያው ይዞታ ዓረብ ፋቂህ የኛን የጦርና ያስተዳደር ሹማምንት ደገል ሃንን ማኅፀንቶን ሮቤልን ተክለ ኢየሱስን "አዝማች" ነው የሚላቸው ። በኛ መቼም ከጥንት ገምሮ በአዝማች ላይ ሌላ የተግባርና የሥፍራ ስም "መርድ አዝማች ፡ ደጅ አዝማች ፡ ቀኝ አዝማች ፡ ግራ አዝማች" ካልተባለ "አዝማች" ብቻውን ሆኖ የማዕርግ ስም ሆኖ ሲሰጥ በታሪክ ውስጥ እምብዛም አልገጠመኝም ። የምጥዋንና የኤርትራን ግዛት ከቱርክ ወርሰው ገዥ የነበሩት ኢጣሊያኖች ላንዳንድ ያገር ተወላጅ የወታደር ሹም አዝማች የሚባለውን ማዕርግ መስጠታቸው ትዝ ይለኛል ።

እላይ ከቢትወደድ ሥርጼ ጋር ከተጠቀሱት ሹማምንት መካከል የኛ ታሪክ ነገሥት ባንድ ቦታ ላይ ተክለ ኢየሱስን በነጠላ ስሙ ብቻ ይጠራዋል (1) በሌላ መጽሐፍ ላይ ግን ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ብሎታል (2) ይኸም ትክክለኛ ነው ። አሁንም የትግሬን ጦር ይዞ የዘመተው በዚሁ ማዕርግ ነው ። ሮቤልን ታሪክ ነገሥቱ ጸሐፊ ላም ሮቤል ይለዋል (3) ። በሌላ ቦታ ላይ ትግሬ መኰንን ሮቤል ተብሎ ይገኛል (4) ። ይኸው ሹም የትግሬ መኰንንነት ሹመት እንደያዘ በተለምዶ ግን ባልጋዳ (በዓል ጋዳ) ሮቤል እየተባለ እንደሚጠራ አልቫሬጽ በመጽሐፉ ያረጋግጣል (5) ።

በዚህ ዘመን ያለው ታሪካችን በጊዜው በደንብ እየተጻፈ ወደ ጊዜያችን ያልደረሰ የተበታተነ በመሆኑ የቀንና ያመት ምሕረት ፡ የቦታና የሰው መጠሪያ ስም የማዕርግ ስም በሙሉ የተጣራ አድርጎ ለማቅረብ ችግር ነው ። የማዕርጉ ስም የሚሳከረውም ላንዱ ሰው በየጊዜው ልዩ ልዩ ማዕርግ ይሰጠዋል ። ወደሌላ ሥራም በተዛወረ ጊዜ አዲሱ ሥራ የማዕርግ ስም ባያጣም የፊተኛው ይበልጥ እንደሆነ ያንኑ የፊተኛውን ይዞ ይጠራበታል ። የዘመኑም ጸሐፊ በአእምሮው ለጊዜው የተደቀነውን ስም ይዞ በመጻፍ ይጓዛል ።

ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ ባዔ ምኒልክ ዘመን የጦር ሚኒስትሩ ሀብተ ጊዮርጊስ ፊታውራሪ ተብለው የራስ ወርቅ አሥረው የራስ ማዕርግ ሲያገኙ መጭው ትውልድ የፊታውራሪውን ደረጃ በማሰብ ከደጃዝማቾች በታች አድርጎ ሳይገምታቸው አይቀርም ። በቅርብ ጊዜ ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ በንቡረ ዕድነታቸው ላይ ያሩሲ ጠቅላይ ገዥ መሆናቸው በደንብ ምክንያቱ እየተለየ ካልተላለፈ ለመጭው ትውልድ ማስቸገሩ የማይቀር ነው ። ወደ ዋናው ሐሳባችን እንመለስ ።

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92
(2) Liber Axum-Conti-Rossini 34-36
(3) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92
(4) Liber Axum 31
(5) አልቫሬጽ ነአቶ ግርማ ትርጉም ምዕ. 45 ገጽ 97

ISIC

ባሁኑ ጊዜ ቢትወደድ ሠርፄ ማዕርጉ እንደ ደገልሃን ትልቅ መሆኑን ማኅፀ ንቶ የደዋሮ ገዥ (ደዋሮ ነጋሽ)፤ አውራይ ኡስማን የፈጠጋር ገዥ፤ ተክለ ኢየሱስ የትግሬ ገዥ መሆናቸውን ጽሑፉ ይገልጻል ። በዚህ ዓይነት ቢትወደድ ሠርፄ፣ ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ፤ ጸሕፈ ላም ሮቤል ከውጭ መጥተው ለዕርዳታ የተጨ መሩ ሲሆኑ፤ ሕዱግ ራስ ማኅፀንቶ የደዋሮ ገዥ (ከራስ ነቢያት በኋላ) አውራይ ኡስማን የፈጠጋር ገዥ ስለሆኑ ይኸው ግራኝ የዘመተባቸው አውራጃዎች የነርሱ ግዛት ነው ማለት ነው ። በተለይ ግራኝ አሁን በከሰምና በዱከም ወንዝ በኩል መጣ ስለሚል ዛሬ የረር ቡልጋ ምንጃር የሚባለው ሁሉ ያን ጊዜ ፈጠጋር ይባላል ። ከርሱ ወደ ምሥራቅ ከባሌ ወደ ሰሜን ከሐረር ወደ ምዕራብ ያለው የከረዩ ወረዳ ሁሉ ደዋሮ መባሉን ከዚህ በፊት አውስተናል ።

እነዚህ ሁሉ ታላላቅ መኳንንት ከዚህ አሁን ከምናነበው ከባደቄው ጦርነት በኋላ ወደፊት ተክለ ኢየሱስ በአይፈርስ ጦርነት ፤ ማኅፀንቶና ሮቤል በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ሲሞቱ፤ አውራይ ኡስማን በብዙ ቦታ ላይ ሲዋጋ ከቆየ በኋላ ግራኝ እየቀናው ሲሄድ ተመልክቶ በመጨረሻ ለግራኝ ገብቶ በአምባ ግሼን ጦርነት ከክር ስቲያኖች ጋር ሲዋጋ ሞተ ። ቢትወደድ ሠርፄ ግን ካፄ ልብነ ድንግል ጋር ሆኖ እየ ተዋጋ ብዙ ጊዜ ቆይቶ የግራኝ ጦር የአምባ ግሼንን ተራራ የከበበ ጊዜ በውጊያ ቀን ተት ገራድ ማታንን ገድሎ አህሙሽን ማርኮ ለንጉሡ ግዳይ ጥሏል ። ሁሉንም በየ ሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ። በዚህ በባደቄ ጦርነት[illegible]ዚህ ከጠቀስናቸው መኳ ንንት በቀር ሌሎች አሴር፤ እሮን፤ ፍቅረ ኢየሱስ፤ ዋሽ ኡስማን የሚባሉ አሉ ። ይህ የመጨረሻው ዋሽ ኡስማን እንደ አውራይ ኡስማን በፊት እስላም ስለነበረ ዓረብ ፋቂህ ስለሁለቱም ሲጽፍ "ከሐዲዎቹ" የሚል ቃል ይጨምራል ።

እንግዲህ ንጉሡ ከባደቄ ወደቤተ አምሐራ ሲሄዱ የባደቄ ከተማ ያለበት የፈ ጠጋር አውራጃ ሹመቱ የአውራይ ኡስማን ስለሆነ እርሱ እየተከላከለ እንዲቆይ አድርገዋል ። በኋላ ግን እነቢትወደድ ሠርፄ እነሕዱግ ራስ ማኅፀንቶ እነትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ሲጨመሩ እነዚህን ሁሉ የበላይ ሆኖ የሚያዘምተው የት ኛው እንደሆነ አይታወቅም ።

የሆነ ሆኖ አሁንም ግራኝና ሠራዊቱ ዣን ዘላቅ (1) ከሚባለው ሥፍራ ተንቀ ሳቅሰው የክርስቲያኑ ጦር ያለበትን ለማወቅ በየመንገዱ ያገኙትን እየያዙ እየመረ መሩ ሞጀ ወንዝ አጠገብ መጥተው አደሩ በማግሥቱ ማሲን . . . . . ከሚባል መን ደር ገብተው የንጉሡን ቤት ክርስቲያንና መንደሩን አቃጠሉ ። በ፫ኛው ቀን የን ጉሡ መኖሪያ ቤትና ሀብት ወደሚገኝበት ወደባደቄ ደርሰው የንጉሡ ጦር ሠራዊት የት ነው እያሉ ቢመራመሩ ሰው ሁሉ በባደቄ ጦር የለም እያለ ደብቋቸው ስለነበረ ከሚጓዙባቸው ፈረሶች ወርደው በበቅሎ ላይ ተጋብተው ተዝናንተው ሲጓዙ ከክር ስቲያኑ ጦር ሠራዊት ጋር በድንገት ተያዩ (2) ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 100 - 105
(2) " " " 114

ዓረብ ፋቂህ እንደሚለው ንጉሡ ጦር ሰብስበው ለመመለስ ከባደቁ ወደቤተ እምሐራ በሄዱ ጊዜ እስከመለስ ድረስ እስላሞቹ ከከተማው ገብተው ማቃጠል ካልዠመሩ በቀር እንዳትዋጉ የሚል ትእዛዝ ስለነበረ የእስላሞቹ ጦር በታየ ጊዜ እላይ በጠቀስናቸው የክርስቲያኖቹ ሹማምንት ዘንድ የአሳብ መለያየት ተፈጠረ ። ግማሾቹ ንጉሡ እንዳዘዙት እስላሞቹ ከከተማው ገብተው ማቃጠል ካልዠመሩ በቀር ጦርነቱን አንዠምርም ብለው ለብቻቸው ተለዩ ። የቀሩት የትግሬ ሹማምንት እነ ሮቤል እነአሴር እነአሮን እነፍቅረ ኢየሱስ እነዋሹ ኡስማን በሕይወት እያለን ቤተ መንግሥቱና የእኅታችን ቤተ ክርስቲያን አይቃጠልም ። እኛ ከሞትን በኋላ ግን እስላሞቹ የፈቀዳቸውን ያድርጉ ማለታቸውንና የእኅታችን ቤተ ክርስቲያን የሚሉት ይኸን ቤተ ክርስቲያን አሣምራ ያሠራችው የንጉሡ እናት (ናዖድ ሞገሳ) መሆኗን ይገልጻል (1) ።

የቀረውን የጦርነቱን ታሪክ ይኸው ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ይተርካል ።

«ከዚህ በኋላ ኃይለኛው ሮቤል . . . . . እፈረሱ ላይ ወጣ የቀሩትም የትግሬ ሹማምንት እነ አሴር እነ ፍቅረ ኢየሱስ ተከተሉት ። በነርሱም ውስጥ የሚታዘዝ ብዙ ወታደር አለ ። ወደፊት ተጉዘው እባደቁ ከተማ በር ደረሱ ። በነርሱና በእስላሞቹ ጦር መካከል ሰመርማ የሚባል ወንዝ ነበር ፤ ክርስቲያኖቹ እወንዙ ድረስ እየተጓዙ መጡ ። ተዋጊውንም ወታደር ማጥቂያውንና መከላከያውን (ጦር ወይም ጐራዴና ጋሻ) መሣሪ[illegible]ዘው ለውጊያ አሰለፉት ።

እስላሞቹም ወደ ከተማዪቱ ተጠግተው ክርስቲያኖችን ባዩ ጊዜ ለውጊያ ተዘጋጁ ። ይማም አህመድ "እፈረሶቻችሁ ላይ ውጡ ነገር ግን ለውጊያ አትጣደፉ በቶሎ ለፈረሰኛ ጦር ውጊያ የሚስማማውን ሥፍራ መርምራችሁ ምረጡ" ብሎ ተናገረ ። ከንግግሩ በኋላ አዶሌ አዝማች ሆኖ ከፊት ቀደመ ። ይማም ሐምሳ ፈረሰኞች ሁለት መቶ የግረኛ ወታደሮች ጉብዝናቸው የታወቀ የተሳለ ሰይፍና የሕንድ አገር ጋሻ የያዙ አስከትሎ ከኋላ ነበር ። እነዚህም ፪፻ ዠግኖች በማናቸውም ጦርነት ጊዜ ከይማም ኋላ የማይለዩ (ጋሻ ዣግሬዎች) ናቸው ። ሁሉም ለውጊያ ከተሰለፈና ፈረሰኛውም እፈረሱ ላይ ከወጣ በኋላ ስለ ሃይማኖታቸው እንዲዋጉ ሲል "እናንተ ሃይማኖት ያላችሁ ሁሉ ታጋሽ ሁኑ ፤ ጦርነቱን አጥብቃችሁ ቀጥሉ ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ ፤ በደስታ እንደምትኖሩ እርግጠኞች ሁኑ" እያለ እስላሞቹን በዲስኩር አነቃቃቸው (2) ።

ከርሱ ቀድሞ የሄደው ወዚር አዶሌ ግን ከነጦሩ ሁለቱን ጦር ይለይ የነበረውን ወንዝ ተሻገረ ። ወንዙን መዠመሪያ የተሻገረ ሳብራህ የሚባል የጋንዝ (ግንጭ) ተወላጅ ነው ። እርሱም . . . . . በክርስቲያኖቹ ላይ ተወርውሮ ጦርነቱን ሲዠምር የቀሩትም እስላሞች እንደ አንድ ሰው ከርሱ ጋር ተባብረው ገቡለትና እግረኛውም ከእግረኛው ተደባልቆ ይዋጋ ዠመር ። የቀኙ ዘማች ሽሽት ሲዠምር

(1) ዓረብ ፋቂህ 114

(2) ቁራን ሱራት 3 ቍጥር 200

የግራው ዘማች በአለቆቹ በነሮቤል ፣ በነአሉር ፣ በነፍቅረ ኢየሱስ እየተመራ ጦርነቱን በመቀጠል የጦር ሰንደቅ ዓላማውን ገትሮ ለምዱን ጥሩሩን እንደለበሰ እንደ ማይገፋ ተራራ ሆኖ ደህና አድርጎ መከተ ። በዚህ ጊዜ ቀጭኑ አቡበከር ከእሮን ጋር ተጋጥሞ ይደባደቡ ነበር አቡበከር በጦር ክፉኛ ወግቶ የጦሩ ጫፍ . . . . . . በጀርባው ወጣ ። እሮን ግን ከኮርቻው ሳይወድቅ ጠብቆ ይቀጥል ነበር ። አንድ የክርስቲያኖቹ አለቃ ደግሞ አቡበከርን ገጠመና ቀኝ እጁን መትቶ ሰበረው ። ነገር ግን እስላሞቹ አሥረው አሥፍረው መለሱለት ። አንዱ የእስላሞች አለቃ ኩሽም አቡበከር ከአንዱ የክርስቲያኖች አለቃ ጋር ተጋጥሞ በሰይፍ ትከሻውን ቢመታው ክርስቲያኑ ብረት ለበስ የሆነ ጥሩር ለብሶ ነበርና ምንም አልሆነም ። ደግሞም ሁለተኛም ሦስተኛም ጊዜ ቢመታው አልሆነለትም ። በዚያን ጊዜ ከሐዲው ዋሹ ኡስማን አቡበከርን ደረቱን ቢመታው የጦሩ ጫፍ በጎኑ ወጣ አቡበከር ግን ከመገጠሚያው አለቃ ጋር ሲደባደብ ነበር ። ከኮርቻውም አልተንቀሳቀም ። በጦርነቱ ላይ ገራድ መንሱር ነፃ ያወጣው (ባርያ) ማርፉ ናስር ቤን አዳም . . . . . ፣ ኤስሲዲቅ ፣ ዲል ሳባር ሞተ ። ዲል ሳባር (ድል ሰበር) በእግሩ ሆኖ እፈረስ ላይ የነበረውን ክርስቲያን እግሩን ይዞ ዘርጥጦ ለመጣል ሲተናነቅ ከኋላው አንድ የክርስቲያን ወታደር ደርሶ ከጀርባው በጦር ቢወጋው የጦሩ ጫፍ በደረቱ ብቅ አለና ወዲያው . . . . . ሞተ . . . . . . ። አቡበከርና ኩሽም ምንም ቁስላቸው ቢጸናባቸው ከተዋጉ በኋላ ጓደኞቻቸው የሞቱ መስሏቸው ጀርባቸውን አዙረው ሸሹ ። የቀሩትም እስላሞች እነሱን ሲያዩ እየሸሹ ሁሉም ወደ ይማም ሃ.ዷSI©ማሾቹም ወንዙን ሲሻገሩ እየሰጠሙ ሞቱ ። ክርስቲያኖቹም ብዙ ፈረሶች በምርኮ አገኙ ።

ይማም አህመድ የሚሸሸውን ጦሩን ባየ ጊዜ ወደ እነርሱ መጣና እየተማታ እንደዚህ አላቸው "ወዴት ነው የምትሸሹት ? ከመንግሥተ ሰማያት ርቃችሁ ትሸሻላችሁን ? ዕድል ከወሰነው ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል ?" ወዲያው ከፈረሱ ወርዶ እመሬት ላይ ተቀምጦ እስላሞቹም ከየፈረሳቸው እየወረዱ እርሱን ከበው በጉዘን ይንጫጩ ነበር ። ይማም የተቀመጠበት ቦታ ለፈረሰኛ ጦርነት የማይመች ጠባብ ሥፍራ ነበር ።

በዚህ ጊዜ ኢሚር ሁሴን "የእስላሞች ይማም ሆይ እንደ ነቢዩ መሐመድ ጓደኞች እንደ ዓረቦች እንዋጋለንና አሁን ድንኳንህን አስተክል" ብሎ ነገረው ። ይማም ድንኳኑን በዚች ሥፍራ አስተከለ ።የሚሸሹት እስላሞች የተተከለውን ድንኳን ሲያዩ ግማሾቹ ልባቸው ጸና ። ክርስቲያኖቹም እስከ ወንዙ ድረስ መጥተው እስላሞቹም ወደ ወንዙ መጥተው እንዳይጠጉ ፈልገው እስላሞቹን ሲወጉ ተዋጊዎቹም መልሰው ሲመክቱ ቆዩ ፣ የወንዙ መሻገሪያ ሥፍራ ሦስት ስለነበረ ይማም አህመድ ጦሩን ሦስት ላይ ከፍሎ አንደኛው ያንኑ ይማም ያለበትን የመካከለኛውን ሥፍራ ያዘ ። ሁለተኛው በሱማሌዎቹ ባላባት በማታን የሚመራው በቀኝ ያለውን የላይኛውን ያዘ ። ወዚር አዶሌ በግራ በኩል ያለውን የታችኛውን ያዘ ። እነዚህ ሦስቱም የየራሳቸውን ጦር ይዘው በየሥፍራቸው መዋጋት ጀመሩ ። በቀኝ በኩል ማታን በሚያዝበት በኩል አንድ ጊዜ ሲገፉ አንድ ጊዜ ሲመለሱ ከረፋድ ጀምረው

እስከ አስር ድረስ ቆዩ (1) ። በዚያን ጊዜ ማታን እርዳታ ላክልኝ ሲል አቡበከር የሚ ባል ፈረሰኛ ወደ ይማም ላከ ። ይማም አህመድም ከፈረሰኞች ውስጥ ጎበዝና ምርጥ የሆኑትን ፈረሰኞች ላከ ። እነርሱም ዋኖቹ ኢሚር (ገራድ) አህሙሽ ፥ ወዚር ኑር ቤን ኢብራሂም ፤ ፋራቀሃም ሱልጣን ፤ አውራይ ኑር ፋራቀሃም ፥ ዲንቤት አዳም ናቸው ። እነርሱም ሔደው ከማታን ጋር ሆነው ምሽት እስኪገላግላቸው ድረስ በር ትተው ቆዋጉ ። የዚህ ቀን ውጊያ በጣም የበረታና ብዙ ደም የፈሰሰበት ውጊያ ነበር ።

ይማም አህመድ ባዘመተበት በመካከለኛው በኩል እንደዚሁ ጦርነቱ የበረታ በርሱም ግንባር ሆኖ በሚያስደንቅ አኳኋን ይዋጋ የነበረው ጎምዛህ ኤል ጁፊ የሚ ባል የዓረብ ተወላጅ ነው ። እርሱም ከእግረኛ ጦር ውስጥ ነበር ጎምዛህ በወንዙ ዳር ከክርስቲያኖች ጋር እየተዋጋ በይማም ፊት ከክርስቲያኖቹ ብዙዎቹን እየመታ ሲጥል የወንዙ ውኃ ከደም ብዛት የተነሣ ወደ ቀይነት ተለወጠ ። ይማምና አጠ ገቡ ያሉትም ከርሱ በኋላ ሆነው ስለርሱ ብርታትና ደህንነት ይጸልዩ ነበር ፤ እር ሱም ጸንቶ ሲዋጋ ምሽት ገላገለው ።

በግራ በኩል ወዚር አዶሴ በአዘመተበት በኩል በቀስት የሚዋጉት መሪሃን የሚባሉት የሱማሌ ነገዶች ነበሩ ። እነርሱም ሲሸነፉም ሲያሸንፉም ብዙ ጊዜ ተዋጉ። ከክርስቲያኖቹ ወገኖች ኢልማያ የሚባሉ መርዘኛ በሆነ ቀስትና ፍላጻ የሚዋጉ ነበሩ ።

ISIC

ይማም "በቀስት ፍላጻ የወረጠሩባችሁ እንደሆነ እየለቀማችሁ ያዙ ። እመ ሬት የተዋቻሁት እንደሆነ ደግሞ ክርስቲያኖቹ አግኝተው እየለቀሙ እንደገና ለውጊያ ይጠቀሙበታል" ብሎ እስላሞቹን አዞ ነበርና ማታ የጦርነቱ ፍጻሜ ሆኖ ወደሠፈር መልስ ሆኖ እያንዳንዱ ኢሚር ብዙ እቅፍ ፍላጻ እየያዘ ገባና እይማም ፊት አስቀመጠው ። ይማም እዋናው ግምጃ ቤት እዳኬል ዘንድ ተሰብስቦ እንዲቀመጥ አዘዘ ። ወይማታ ሲሆን አንድ ላም ታረደችና ማብሰያ እንጨት ጠፋ በዚያን ጊዜ ዱኬል ለጓደኞቹ እንደዚህ አለ "ይኸው ፍላጻ ነገ ክርስቲያኖቹ ቢማርኩን አግኝ ተው እንደገና ከሚጠቀሙበት ለምን በዚህ በፍላጻው እሳት አንድደን ሥጋችንን አናበስልም" ጓደኞቹም እውነትህ ነው ብለው በፍላጻው ሥጋቸውን ጠበሱ ..... ።

የቀኑም ጦርነት ለእስላሞቹ አዋኪ ሆኖ ስለዋለ አንዳንድ እስላሞች ሃይማኖ ታቸውን እየካዱ ወደ ክርስቲያኖቹ ዘንድ ገቡና ክርስቲያን ሆኑ ። አንዳንዶቹም እየጠፉ ሌሊት ወደ አገራቸው መመለስ ሲገርምሩ ይማም በነገር እየቀሰቀሰ ለጦር መሸሽ ለፈለጉት "በሌሊት እየጠፋችሁ አትሒዱ ክርስቲያኖቹ ስትሸሹ እመን ገድ ይፈጅዋችኋልና ምናልባት አምላክ እርዳታውን ይልክላችኋል ጠንክሩ በርቱ እግዚአብሔርንም ፍሩ ምናልባት ሳታሸንፉ አትቀሩም አላቸው ። ነገር ግን ጧት ሲነጋ ድምሩ ወታደር ሽሽት ዠመረ ። በይማም አህመድ አጠገብ ከዓርባ የጎበዝ

(1) እስር ቀጥር ሰዓት ወይም አስር ሰዓት ይመስላል

ፈረሰኞች ከሐያ ከታወቁ የጎበዝ እግረኛ ጦር ባጠገቡ ጠፋ ። ይማምና ጓደኞቹ በራ
ሪዎቹን ለመመለስ ሮጡ ። ቀጥሎ ከነጋ በኋላ ዓሊንና ወዚር ኑርን ቀድማችሁ አፈት
ሐዶና ሲሸሽ የምታገኙትን እስላም ሁሉ ግደሉ አላቸው ። እነርሱም በሩጫ አፈት
ቀድመው ዱከም ወንዝ አጠገብ የሚሸሸውን ከመንገድ ይዘው አራት ሰው ገደሉ ።
ለቀሩትም ወዴት ነው የምትሸሹት የሸሻችሁ እንደሆነ ልንገድላችሁ ሥልጣን
ተቀብለናል ። ስለዚህ ተመልሳችሁ ጠንክራችሁ ተዋጉ ከክርስቲያኖች ስትዋጉ
ብትሞቱ መንግሥተ ሰማያትን ፤ በሕይወት ብትኖሩ ደስታን ታገኛላችሁ እያሉ
ሲሰብኩዋቸው ይማም ደርሶ ብዙ የሚሸሹትን አግኝቶ ገደለ አንዳንዶቹንም አቆ
ሰለ ። ሕግ አዋቂው ሊቁ ሲዲ አቡበከር አርሹናህ "በእግዚአብሔር ፈቃድ ትንሽ
ጦር ብዙውን ያሸንፋል እግዚአብሔር ጦርነትን ታግሦ ከሚቀጥለው ጋር ነው"
ብሎ ለሚሸሹት ከቁራን ቃል እየጠቀሰ ተናገረና ወደ ጦርነቱ እንዲመለሱ አደረ
ጋቸው ። በዚህ ቀን ይኸው ሲዲ አቡበከር እወንዙ አጠገብ በቀስት ተመትቶ ነበር
ነገር ግን ዳነ ። ይማም አህመድ በበኩሉ "የእስላሞች አገር ወዴት ነው ከክርስቲያ
ኖቹ አገር ሩቅ አይደለምን አሁን በእግዚአብሔርና በሰይፋችሁ ኃይል ካልሆነ
በቀር መዳኛ የላችሁም ፤ ከክርስቲያኖቹ ፊት እንዴት ትሸሻላችሁ . . . . ." እያለ
ተናግሮ አጸናቸው ፤ አበረታቸው ። በዚያን ጊዜ የሱማሌዎቹ ነገዶች የሀርላህ ነገ
ዶች ናቸው ያጋለጡን ብለው ተናገሩ ፤ የሀርላህ ደግሞ የለም የሱማሌዎቹ ናቸው
መዝመሪያ ያጋለጡን ብለው መለሱ ። በዚያን ጊዜ ይማም ከሦስት ላይ ከፋፈለና
ሱማሌዎቹን ለማታን ፤ የሀርላህን ሰዎች ለሱልጣ[illegible]ሐመድ ሰጣቸው ። ሦስተ
ኛው ለውጊያ የታመነው የመለሳይ ዘር ነው የይማም ዘር ከነርሱ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ክርስቲያኖቹ እሥፍራቸው ሆነው እግዚአብሔር እስላሞ
ቹን ለማንሣት ክርስቲያኖቹን ለማዋረድ አስቦ ኖሮ በመካከላቸው ክርክር ተፈጥሮ
ነበር . . . . . ግማሾቹ እስላሞቹ ይኸው መከላከላቸውን ትተው ሽሽት ይዘዋልና
እየተከታተልን እንውጋቸው ሲል ግማሹ እስላሞቹ እኛን ከሥፍራችን ወጥተን
ወደነርሱ ስንጠጋ መልሰው ለመውጋት ተንኮል አስበው ነውና የሸሹትን ባንከተል
ይሻላል አለ ፤ የቀረው ደግሞ ንጉሡ እስኪደርሱ ድረስ ዝም ብለን የያዝነውን
ሥፍራ ብቻ አጽንተን እንያዝ ንጉሡ ዛሬ ጧት ስለሚገቡ ድንገት እስላሞቹን ስና
ባርር የተሸነፍን እንደሆነ እቅርብ መሆኔን እያወቃችሁ እኔን ሳትጠብቁ ለምን ተዋ
ጋችሁ ብለው ይቆጡናል ስለአሉ ሁሉም የነዚህን የመጨረሻዎቹን አሳብ ተቀብሎ
ተቀመጠ ።» እያለ ዓረብ ፋቂህ የባደቄን የጦርነት ታሪክ እዚህ ላይ ያቆማል (1) ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 105 - 112

## ምዕራፍ ፴፮

## በአሳብ መለያየትና በሰላ ጉድለት የተነሣ የግራኝ ወረራ መቃናት

የባደቄ ጦርነት ለት የተገኘው ድል ለግራኝ አህመድ ውድቀት መልካም አጋጣሚ ምክንያት አቅርቦ ነበር ። በዚህ በመልካሙ አጋጣሚ ምክንያት ክርስቲያኖቹ ዕለቱን በዚያው የግራኝ ጦር በሸሸበት ሰዓት የዱክምን ወንዝ እየተሻገሩ አባርረው ስላልተጠቀሙበት ግራኝ አሁንም ጦሩ ከተሸነፈ በኋላ የማያባርረው ጽኑ ጠላት በማጣት እንደገና እንሥራርቶ የፈረሰውንና የሚሸሸውን ጦሩን በማባበልም በድብ ደባም አቁሞ ወደፊት እንደምናነበው እንደገና ሽምብራ ኩሬ ላይ ንጉሡ ነገሥቱን አሸንፎ ግዛቱን ሊያረጋግጥበት መቻሉ በባደቄ የፈሰሰው የገሮግኖቹ ደምና ድል አድራጊነት ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ከማስገረም ጋር ያሳዝናል ።

እስላሞቹ በባደቄ ተሸንፈው በሚሸሹበት ጊዜ ከኋላቸው አባራሪ ጦር ሳይከተላቸው ስለቀረ ራሳቸውን ገርሟቸው ኖሯል ። ስለዚህ ባለፈው እንዳነበብነው ዓረብ ፋቂህ «እግዚአብሔር እስላሞቹን ለማንጣት ክርስቲያኖቹን ለማዋረድ አስቦ በመካከላቸው ክርክር ተፈጥሮ ነበር» ያለው የሚታመን ነው ። ግማሾቹ እስላሞቹ ይኸው ሸሽተዋልና እናባርር ሲሉ ግማሾቹ የለም አይሆንም እኛ ከሥፍራችን ወጥተን ወደነርሱ ስንጠጋ መልሰው ለመውጋት ተንኮል አስበው ነውና ባንከተል ይሻላል አሉ የቀሩት ደግሞ ንጉሡ እስኪመጡ ድረስ የያዝነውን እናጽና እንጂ ንጉሡ ዛሬ ስለሚገቡ ድንገት እናባርር የተሸነፍን እንደሆን እቅርብ መሆኑን እያወቃችሁ ለምን ተዋጋችሁ ይሉናል ስላሉ ሁሉም በዚሁ ተስማሙ ያለውን መልሰን እናስታውሳለን ። ዓረብ ፋቂህ ይኸን ሁሉ የሌለበትን የኛን ወገን ዝርዝር ወሬና ጉድለታችንን እየጨመረ የሚያቀርብልን ከሽምብራ ኩሬ ድል በኋላ በምርኮኛነት ከሚያገኛቸው የጦር ሹማምንቶች መሆኑን ራሱ በጽሑፉ ያረጋግጣል (1) ።

በዚህ በባደቄ ጦርነት የኛ የጦር አለቆች በልዩ ልዩ አሳብ በመለያየት ፈንታ ለጠላቶቻቸው ዕረፍት ሳይሰጡ ወዲያው ተከታትለው እያባረሩ ወግተዋቸው ቢሆን ኖሮ ግራኝ አህመድ ምንም ገሮግና ቢሆን ከተሸነፈና ተዘበራርቆ ከሚሸሸ ጦር ጋር ምንም ማድረግ አይችልም ነበር ። የራሱም ሕይወት በፈረስ ግልቢያ ካላ መለጠ በቀር ወጣ ገባውን በማያውቀው በፈጠጋር ግዛት በአደጋ ላይ በተገኘ ነበር ። የርሱም ሕይወት ከሌለ የተከተለው ሕዝብ አብዛኛው በግዴታ ጭምር የመጣ ስለሆነ ከወዲህ ከጠላት ወገን እየተዋጋ ከወዲያ ከግራኝ በኩል ተመለስ ተዋጋ እየተባለ አንድ ጊዜ በድብደባ ሲገደድ አንድ ጊዜ ጠንክረህ ብትዋጋ መንግሥት ሰማያትን ታገኛለህ እየተባለ ቢተባበልም ምንም ማድረግ አይችልም ነበር ።

በዚህ በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግልና መኳንንቶቻቸው መተባበራቸው በገሮግንነት መዋጋታቸው ሳይቀር የሚያውቁትን የዘመኑን የጦርነት መላ በጥብቅና በትጋት የተከተሉት አይመስልም ። ከዘመኑ የጦር መላ ውስጥ አንዱ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 116

እንደምንም ብሎ የጠላትን ጦር አለቃ መግደል ነው ። የዚህም ጠቃሚነት አለቃ ቱው ሲሞት በውድም በግድም የተሰለፈው ወታደር ተስፋ በመቁረጥ በግድም በውድም እየታዘዘ የመጣው ጦር አለቃው ሲወድቅለት ወይም ሲወድቅበት መሸሹ ስለማይቀር ነው ። እንደዚሁም ለዚያን ጊዜም እንደ ዛሬው ዘመን በጦርነት ሰዓት የሚያስፈልገው የስለላ ሥራ ነው ። ለማናቸውም ለግለኛ ሰው ለቀለም ሰው ስሜት ላለው ፍጡር የስለላ ሥራ ቅር የሚያሰኝ ሲመስል በኃይሌ በሥልጣኔ እኖራለሁ ጠላቴን አሸንፌ አገር እገዛለሁ ለሚል ንጉሥና የመንግሥት መሪ ወይም ሊወረኝ የመጣውን ተከላክዬ እመልሳለሁ ለሚል ለሁለቱም ወገን የስለላ ሥራ ዋና ጠቃሚ ነው ። የጠላቱን ኃይልና ድካም አውቆ መዋጋት የድል ፍቱን መድኃኒት ነው ። ያዔ ልብነ ድንግል መንግሥት ያዳሎችንና የሱማሌዎቹን የጦርና የውስጥ ሁኔታ እያሰለለ ከስለላ በሚያገኘው ፍሬ በጣም የተጠቀመ አይመስልም ። ባንዳንድ ነገር ቢጠቀምም ብዙ ሳያውቀውና ሳይጠቀምበት የቀረ መሙላቱን ከባይቁው ጦርነት በቀር ባለፈው ከሡልጣን አቡበከር ጋር በተዋጋበት ጊዜ ያመለጠው አጋጣሚ ምክንያት የሚታወስ ነው ።


ከአራት ዓመት በፊት የደዋሮ አገረ ገዥ ፋኑኤል ከግራኝ አህመድ ተዋግቶ ግራኝ ሐረር ከተመለሰ ወዲህ ብዙ ጊዜ ከሐረሩ ሡልጣን እየተጣሉ እርስ በርሳቸው መዋጋታቸው የታወቀ ሲሆን ዓፄ ልብነ ድንግል አስያይቶህ ግዛ የተባለውን የሮማውያንን ፍልስፍና መሠረት አድርገው በሁለቱ ጠበኞች በግራኝ አህመድና በሡልጣን አቡበከር መካከል ገብተው ላንደኛው ረዳት ሆነው የአንደኛውን ኃይል ማድከም ይችሉ የነበረውን ምንም ስለዚህ ጉዳይ የወሰዱት እርምጃ በጽሑፍ ላይ ሠፍሮ የተገኘ ስለሌለ አልሞከሩም ማለት ነው ። ከዚያ የበለጠ ደግሞ የግራኝ አህመድ ጠላትነትና አጥቂነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገለጠ ሲሔድ ይልቁንም ባሁኑ በባይቁ ጦርነት ላይ እንቢትወደድ ሡርዔ ፡ እነ ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ፡ እነጸሕፈ ላም ሮቤል ክፉኛ ተዋግተው የግራኝን ኃይል ሰብረው የሱማሌ ወታደር በድምሩ የጦርነቱን ግንባር አፍርሶ ሸሽቶ አገሬ ልግባ እያለ ሲሮጥ ግራኝና ጓደኞቹ ተመልሰህ ተዋጋ እያሉ ሲደበድቡት በዚህ ዓይነት የተዘባረቀውን የግራኝን ጦር ሁኔታውን አለልለው እያባረሩ በመውጋት በዚህ መልካም አጋጣሚ ምክንያት አልተጠቀሙበትም ። ይኸም በጊዜው አጭርነት ምክንያት የሚርቅባቸውና ምሥጢሩን ማግኘት የሚያዳግት ቢሆን ግራኝ ያለበትን ጦር እንደምንም በሌላ መስመር ቀጥሩ የበረከተ አዲስ ጦር አስመጥቶ በመውጋት አሸንፎ ግራኝን ማጥፋት ይቻል የነበረውን ምንም እንኳን ዓረብ ፋቂህ መሞከሩን ባንድ ሥፍራ ላይ ቢያወሳ በቀጥሩ ማነስ ምክንያት ተሸንፏል ። የጦር ሹማምንቶቻቸውን ወደፊት ባደቁ ልከው እያዋጉ ንጉሡ ነገሥቱ ብዙውን ጦር እንደያዙ ቤተ አምሐራ መቆየት ብቻ ሳይሆን እኔ እስክመጣ እየተከላከላችሁ ብቻ ቆዩ ያሉት ትእዛዝና እርሳቸው ሳይመጡ የተዋጉና የተሸነፍን እንደሆን ይቆጡናል የሚለው ሥጋት ዞር ዞር ወደፊት እንደምናንበው ለጠላታቸው ጠቅሞ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ራሳቸውን ንጉሡን ከመሸነፍና ከመሸሽ አድርሶ መልሶ ጐድቷቸዋል ።

በማናቸውም አጋጣሚ ምክንያት መጠቀም የሚያውቀው ወጣቱ ግራኝ አህመድ ግን በባደቁው መሸነፍና በንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ባለው ጊዜ ውስጥ ወታደሩን ራሱ እየሰበከ በሊቃውንቱ እያሰበከ ፍርሃት ባፈረሰው ጦር ላይ እንደገና ነፍስ ዘርቶ በሚቀጥለው ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ያሉበትን የጦር ሠራዊት ማሸነፉን ወደፊት እናነባለን ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ግራኝ አህመድ ምንም እንኳን ባለፉት ዓመቶች በ፲፭፻፳፩ - ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. እነደገልሃንን ፡ እነ ወናግ ግርንን ፡ እነአርብ ሺመልን ማሸነፉን ቢያውቁ በአሁኑ ጊዜ ግንባር ቀደም ሆኖ ባደቁ ላይ የተሰበሰበውን ያግራና የትግሬ የጸለምት ጦር ያሸንፋል ብለው የጠረጠሩ አይመስልም ። ምናልባት ለማሸነፍም ቢችል በጣም ከደከመ በኋላ ነውና በከደመው ጦር ላይ የእኔ ቅጥሩ የበዛና አዲስ ጦር ይዞ መድረስ ለድሉ ዘለቄታ ፍጻሜ ይሰጠዋል ብለው ተስፋ ሳያደርጉ የቀሩ አይመስልም ። ዳሩ ግን በባደቁ ያሉት ሹማምንትና መኳንንት ባለፈው ምዕራፍ እንደተገነዘብነው ከግራኝ ጦር ጋር ውጊያ ገጥመው እማባረር ከደረሱ በኋላ ጠላቶቻቸውን እስከመጨረሻ በማሳደድ ፈንታ ንጉሣችንን ብንጠብቅ ይሻላል ብለው እከተማዪቱ ምሽግ ውስጥ እንዳሉ ንጉሡ እከተማዪቱ ገብተው ከነርሱ ተገናኝተው የሽምብራ ኩሬን ጦርነት በሚገምሩበት ጊዜ መካከል እላይ እንጻመለከትነው ግራኝ አህመድ በሽሽት የፈረሰውን ጦር በኃይልም በመንፈሳዊና በዝግንነት አነጋገርም መልሶ አ[illegible]ው ። ከፈረሰ በኋላ የረጋውም ጦሩ ሽሽት ያላሰበውን በንጉሠ ነገሥቱ መሪነት ለድል አድራጊነት የኀኀውን የኢትዮጵያውያንን ጦር በሚያስደንቅና ባልታሰበ አኳኋን ማሸነፉ አስገራሚ ነው ።

ይኸን የመሰለውን አስተያየትና ፍርድ ለመስጠት የሚመራን ባለፈው ምዕራፍ የተጻፈው የዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ነገር ግን ዞሮ ዞሮ በየጦርነቱ ግንባር በሽምብራ ኵሬም ጦርነት አሸናፊው ግራኝ ተሸናፊው ዓፄ ልብነ ድንግል መሆናቸው በኛው ታሪክ ነገሥት የተረጋገጠ ስለሆነ ከጠላት ወገን የሆነ ጸሐፊ የጻፈውም ቢሆን ነገሩ በጠቅላላው ከእውነትነት አልዘለለም ።

ከክርስቲያኖቹ ወገን ዝርዝር ጽሑፍ ቢኖር ኖሮ የትኛው የስለላ መንገድ ወይም የጦርነት መላ ተሞክሮ ሳይሳካ ቀርቶ መሸነፍ እንደመጣ ነገሩን ለማመዛዘን ወይም ጉዳዩን ወደ ሃይማኖት ወስደን ምንም ቢጥሩ እግዚአብሔር ድልን ነሣቸው ንጉሥም በሠራዊት ብዛት አይድንም ወደሚለው አሳብ እንቀርብ ነበር ። ዳሩ ግን ይኸን የመሰለው ለኢትዮጵያ ታሪክ ዓይነተኛ የሆነውን ታላቅ ጦርነት በሰፊው የሚናገር ያገራችን ጽሑፍ ስለሌለ አሳባችንን በዚሁ በላይኛው ከጠላት በመነጨው አስተያየት ለማቆም ግዴታም ውዴታም ነው ። የሆነ ሆኖ አሁን የዚህን ውን የሽምብራ ኵሬን ጦርነት እንመልከት ።




የሐረርንሁሪያ ነጋዶች ከውጭ አገር ከአረብ ከፋርስ ከቱርክና ከሕንድ አገር ከመጡት የእስላም ተወላጆች ጋር በማስተባበር ግራኝ አህመድ ዓፄ ልብነ ድንግልንና ሠራቸውን እየተከታተለ የተዋጋበትን ሥፍራዎች የሚያመለክት ።

## ምዕራፍ ፴፰

### በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዋዜማ በሁለቱ ተዋጊዎች ዘንድ የነበረው ሁኔታና የሰልፍ ዝግጅት (መስከረም - መጋቢት ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ይህ የባደቁ ጦርነት የተደረገበትን ጊዜ ዓረብ ፋቂህ እንደ ዓረቦች አቈጣጠር ፱፻፴፭ ዓመት ፯ ወር የጕደለው ያለውን ሙሴ ረኔ ባሴት ወደ አውሮፓ አቈጣጠር አምጥተው ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. አድርገው ወሩን ከመስከረም ላይ መድበውታል (1)። ጦርነቱ የተደረገበትን ሥፍራ ዓረብ ፋቂህ አንድ ጊዜ ባደቁ አንድ ጊዜ ሽምብራ ኩሬ ብሎት ይገኛል ። ሁለቱም ከተሞች ዛሬ ስማቸውም ሥፍራቸውም የጠፋው ያንጊዜ በዱከምና በሞጆ በዝቋላ አካባቢ መሆናቸው የታሪኩ አነጋገር ያመለክ ታል ።

ምንም እስላሞቹ ከዋናው ከባደቁ የጦር ግንባር ቢሸሹ ይህ ጦርነት በተደረ በት በመስከረም ወርና ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተ አምሐራ ጦር ይዘው መጥተው በተዋ ጉበት በመጋቢት ወር መካከል የስድስት ወር ጊዜ ስለአለ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁለ ቱም ወገኖች እርስ በርስ እየተሰላለሉ ለትልቁ ጦርነት ከመዘጋጀት ጋር አልፎ አልፎ የግልጥም የደፈጣም ጦርነት ሲያደርጉ ሰንብተዋል ። ዓረብ ፋቂህ በመጽ ሐፉ ያንድ ክፍል የክርስቲያን ጦር የሸሸትን እስላሞች ለመክበብ ቀድሞ አንድ ተራራ ይዞ ለመጠበቅ ሞክሮ ሳለ እስላሞቹ ተራራውን ከበው አንድም ሳያመልጥ ሁሉንም ክርስቲያኖች እንደፈጁዋቸው ያወሳል ። ይኸም ባለፈው እንዳልነው ISIC ቍጥራቸው በማነሱ ሳይሆን አይቀርም ።

ከዚሁ አያይዞ እስላሞቹ ከተራራው አልፍ ብለው ዝቋላ አጠገብ ከወንዝ ዳር ሠፍረው ሳሉ ኤልማያ የሚባሉ ነገዶች ንጉሡን ለመርዳት ፱፻ የሚሆኑ ቀስትና መርዝ ያለበትን ፍላጻቸውን እንደያዙ ሲጓዙ በስሕተት የክርስቲያን ሠፈር መስ ሏቸው እስላሞቹ ሠፈር በድንገት ገብተው ሳለ በኋላ መሳሳታቸውን አውቀውት ንጉሡ ወደ አሉበት አቅጣጫ ሲሸሹ እስላሞቹ እያባረሩ እንደፈጁዋቸው የተረፉ ትንም እየማረኩ ከግራኝ ፊት አቅርበው እንደገደሏቸው ። አለቃዩውም ፱፻ ወቄት ወርቅ ከፍዬ ልለቀቅ ቢል ግራኝ «አንተ ውሻ ያንተ ገንዘብ አያስፈልገንም» ብሎ ወዲያው እንዳስገደለው ይገልጸል (2) ።

ይኸው ጸሐፊ የራሱን ወገን በዚህ ዓይነት ካመለከተን በኋላ በክርስቲያኖቹ በኩል ያለውንም ሲተርክልን ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል ከቤተ አምሐራ ተጕዘው ባደቁ መድረሳቸውንና እንደደረሱም ሲዋጉ ለቆዩትና የባደቁን ድል ላስገ ኙት የጦር አለቆች እስላሞቹ ለምን ከተማዩቱ ገብተው እንዲያቃጥሉ አልተዋች ኋቸውም ብለው ቢጠይቁ የትግሬዎቹ ሹማምንት የእኅታችን ቤተ ክርስቲያን መቃጠል አይገባትም ብለው እንደመለሱላቸውና ንጉሠ ነገሥቱም ተዋጊዎቹን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 109 ማስታወሻ ቍጥር 2
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 112 - 114

አመስግነው ለዋነኞቹ ሽልማት እንደሸለሙ ያመለክታል ።

የንጉሡ እናት የሚለው ባለፈው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው እቴጌ ናዖድ ሞገሳን ነው ። እርሳቸውም ባንድ ወገናቸው የደዋሮ ባላባት ልጅ ሲሆኑ በሌላው ወገን የትግሬ ተወላጅ ናቸው ማለት ነው ። በሕይወታቸው ሳሉ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በ፲፭፻፲፫ ወይም በ፲፭፻፲፬ ዓ. ም. የተመረቀ ጊዜ በዚያው አጠገብ እቴጌ ናዖድ ሞገሳ አንድ ቤተ ክርስቲያን (መካነ ሰማያት) አሠርተው ስለነበረ ፖርቱጊዞቹ እንደጐበኙትና ሲጐበኙም ፈርሶ እንደገና ይሠራ እንዳትል መኳንንቱ ሥራውን እንዳንነቅፍ አስጠንቀቁን ሲል አልቫሬጽ በመጽሐፉ ጠቅሷል ። እኚሁ የንጉሡ እናት ካንዱ ቢትወደድ ጋር ወዳጅነት ይዘው ኖረው በኋላ እንደሞቱና እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ቢትወደዱን ንጉሡ ነገሥቱ አሥረውት ሲኖር ከዚያ አምልጦ ወደ አዳል መግባቱን ጨምሮ ያመለክታል (1) ።

ስለዚህ በዚህም በፈጠጋር ከተማ በባይቄ እቴጌ ናዖድ ሞገሳ የሚያምር ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ኖሮ የዘመዳቸው ቤተ ክርስቲያን እንዳትቃጠል ሲሉ በተለይ ትግሬዎቹ በርትተው ተዋግተዋል ማለት ነው ። በገርግንነት ከተዋጉት የትግሬ ሹማምንት ውስጥ ሮቤልን ዓረብ ፋቂህ ደጋግሞ አንሥቶታል ። ይኸንንም ሮቤልን አልቫሬጽ ንጉሠ ነገሥቱ ከትግሬ ሹማምንት ግብር አቀባበላቸውን ሲተርክ "ባልጋዳ ሮቤል የትግሬ መኰንኑ ከግብሰ የመጡ ቁመታቸው እንደዝሆን ታላቅ የሆነ ፴ ፈረሶች አቀረበ" ሲል በመጽሐፉ አ[illegible]ውሶታል ። ይኸም ዝግና መኰንን ከባይቄ ጦርነት ከተረፈ በኋላ በዚሁ ዓመት በመጋቢት ወር በሽምብራ ኩሬ በተደረገው ጦርነት ከሌሎቹ ዝግኖች ጋር ሕይወቱን ላገሩና ለንጉሠ ነገሥቱ መሠዋቱን ወደፊት እናነባለን ።

ግራኝ አህመድ ከሐረር ወደ ፈጠጋር እንደተመለሰ የሃይማኖት ወገኖቹ "ከወገንህ ማንም የኢትዮጵያን ንጉሥ እዚህ ፈጠጋር ድረስ መጥቶ ለመዋጋት የደፈረ የለም ። የንጉሡን የጦር ሠራዊት ቁጥሩንና ልኩን ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለም" በማለት የእስላምን ዘር ሳያስጨርስ ወዳገሩ በሰላም እንዲመለስ የመከሩትን አልፎ ከዚያ በባይቄ ጦርነት ብዙ ሰው ሞቶበት የቀረውም ከመሸሸ ከደረሰ በኋላ አሁን ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው ቀድሞ በነበረው ጦራቸው ላይ አዲስ ጦር ይዘው ሲመጡ ሳይሠጋ እንደገና ወደ ሐረርጌም ሔጄ ጦር ጨማምሬ ተዘጋጅቼ ልመለስ ሳይል ጦርነት ለማድረግ መዘጋጀቱ ምን ያህል በራሱ የተማመነ ዝግና ተዋጊ መሆኑን እንረዳለን ። ከመገርመሪያ አነሣሡ ላይ «ድል ማድረግ ወይም መሞት» መሠረታዊ አሳባችን ነው ብሎ ቆርጧል ። ሱልጣን ተብለህ አትጠራ ይማም ተባል ፤ በዚህ ስም ነው የሀበሻን አገር ልትገዛ የምትችለው ብሎ ከሥር ከእነሣሡ ላይ አዋቂ ነኝ ባይ እንደነገረው ሁሉ አሁንም በዚህ የሂጅራ ዓመት (፱፻፵፫) በመጋቢት ወር ብትዋጋ ንጉሡን ታሸንፋዋለህ ብሎ ያሳመነው አዋቂ እንዳለ አይታወቅም ። ኖሮም እንደሆነ ትንቢቱ ይዞለታል ማለት ነው ።

(1) ምዕራፍ 95

ዓረብ ፋቂህ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት በዋዜማው ቀንና ሌሊት እንደዚሁም ከውጊያ በፊት እስላሞቹ የፈጸሙትን ድርጅትና ግራኝ አህመድ የወታደሩንና የሹማምንቱን ልብ ለውጊያ ለማጽናት ያደረገውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ንግግር በሰፊው እንደዚህ ሲል ይገልጻል ። «እስላሞቹ . . . . . በደሆነኩ የጸሎት ጊዜ ሞጀ ወንዝ ደርሰው ከፈረስና ከበቅሎቻቸው ወርደው ውኃን አጠጡ ። ከዚያ አልፈው ከሽምብራ ኩሬ ወደላይ በኩል ሠፈሩ ። ይህ ሰዓት የረቡዕ ሌሊት ዓመት የሂጅራ ፱፻፴፭ (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) የረገብ (መጋቢት) ጨረቃ የተወለደችበት ሌሊት ነበር ። እስላሞቹ ሁሉ ሌሊቱን የእግዚአብሔርን ስም ሲያነሡ ሲቀድሱ አደሩ ።

ከዚህ በኋላ ይማም አህመድ ከጓደኞቹ መካከል ብድግ ብሎ እግዚአብሔርን በክብርና በምሥጋና እያነሣ ስለነቢዩም (መሐመድ) እየጸለየ ብርቱዎችና ጽኑዎች ናችሁ ብሎ የጦር መሣሪያ እንዲታጠቁ አዘዛቸው ። ቀጥሎም በእግዚአብሔርእመኑ የርሱንም ድጋፍ ፈልጉ ሲል ሠራዊቱ መሣሪያውን ይዞ ጉዞ ገሠመረ ፤ ፈረሰኛውም እፊት ቀደመ ። በዚህ ጊዜ ይማም አሳባችሁ ምንድነው ብሎ ጠየቀ ። ጓደኞቹም ለኛ ምኞታችንም አሳባችንም ጦርነት ነው ። ጠላትን ገትረን ከመዋጋት በቀር የጦርም የሰይፍም በትር ቢበዛብን እግዚአብሔር በዳኝነቱ በመካከላችን ፈርዶ እስኪወስ ደን ድረስ እንላላም ብለው መለሱለት (1) ። በዚህ ንግግር ይማም ደስታ ተሰማው ቸው ። በእንደዚህ ያለ ይብ131ፀጸኦ በኋላ ጧት ጉሀ ሲቀድ ሙአገዚን (ለጸሎት ቀስ ቃሹ) ወደ ምግባራችሁ ኑ ሲል እስላሞቹ ሁሉ ተሰብስበው የጧት ጸሎታቸውን አደረሱ ። ሊቁ ሲዲ አቡበክር በዚህ ጊዜ በብርታትና በትዕግሥት የሚገኘውን ጽድቅ ፤ በፍርሃትና በሽሽት የሚመጣውን ገሃነመ እሳት እየገለጸ ሰበከ (2) ።

ከዚህ በኋላ እስላሞቹ በሽምብራ ኩሬ መካከል አድርገው በምሥራቅ በካናጥ ደግሞ እንደ አንበጣ የበረከተ ጦሩን ይዞ በቁበላህ (ሰሜን ምሥራቅ) በኩል እየተ ቹም አዩት ክርስቲያኖቹም ጉዞአቸውን አቁመው ለውጊያ ሰልፋቸውን እስከ ሰፉ ። አንድ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ከንጉሡ ጋር የነበረ አዝማች ሃይቢ የሚባል እንዳጫወተኝ የንጉሡ ጦር ፲፮ሺ ፈረሰኛ ፤ ቀስትና ጦር ጉራዴ ይዞ የሚዋጋው እግረኛ ሁለት መቶ ሺ ነበር ።

ወደ አማጀህ (አመጃ ወይስ አገምጃ ይሆን ?) ሲሄዱ የሀበሻው ንጉሥ ጓዝ ለአለቆቹም እንዳያመልጡዋችሁ ያዙዋቸው ብሎ አዞ ነበር . . . . . ። እስላም ሰባት ረድፍ ድረስ አድርገው ጫፉ አይታይም ነበር ። እስላሞቹም እንደዚሁ ተሰ

ይማም አህመድ ወደ ፊት ቀደመና በመካከል በቀኝና በግራ የሚዘምተውን አሰለፈ "እዚህ ላለነው ለሁላችንም ጽናትን ስጠን ሃይማኖትህንም እርዳት ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ . . . . " ከዚያ ሱልጣን መሐመድን . . . . . . ፤ ሼክ አን ስን . . . ፤ ለሀርላህ ፤ ለዚመብራሁ ፤ ለባርዛህ ፤ ለያቆላህ ፤ የመራሂሻን ፤ የይበረ ፤

(1) ቁራን ሱራት 7 ቁጥር 85 ሱራት 10 ቁጥር 109
(2) ቁራን ሱራት 3. 5 ቁጥር 200

የሱማሌ ነገዶች ከባላባቶቻቸው ከአህመድ ጀሪ ጋር ሐርቲ ፣ ማይቲ ፣ ጀረን ማዛር ቤርሰብ ሁሉም የሱማሌ ነገዶች በግራ በኩል እንዲዘምቱ ተደረገ ። እያንዳንዱ ነገድ በየአለቃው ይታዘዝ ነበር ። በመካከል ራሱ ይማም አህመድ የኢብራሂም ልጅ እንደ አንበሳ የሚያስፈሩትን ፈረሰኞቹን ይዞ ተሰለፈ ። ከዋነኞቹ ፈረሰኞች ውስጥ ኤሚር ሁሴን ቤን አቡበከር ፣ ኤሚር ዘሀርቡይ መሐመድ ፣ ፋራቃሃም ዓሊ ፣ ወዚር ኑር ቤን ኢብራሂም ፣ ኤሚር ሙጋሂድ ፣ ፋራቃሃም ሱልጣን ፣ አብድ ኢን ናስር ፣ ሸክ ደዋህ ፣ ኤሚር አቡበከር ቀጭኑ ፣ ፋራቃሃም ዲን ፣ ለነዚህም ይማም ከቁራን እየጠቀሰ ዲስኩር ተናገራቸው (1) . . . . . ከነዚህም ጋር የድል ወንበራ ወንድም የማጎፋዝ ልጅ ገራድ አህማጁሽ ፣ አውራይ አህመድ ዲን ፣ ገራድ ሻሙን ፣ በሻርህ ፣ ሳብር ኤድ ዲን ፣ ጋሻ ኡመርና . . . . . . እነዚህን የመሳሰሉ ነበሩ ። ይማም ከርሱ ጋር በብዙ ጦርነት የዋሉትን ከርሱ የማይለዩትን የውጊያ ልማድ ያላቸውን ፳፻ ፈረሰኞች ከፊቱ አስቀደመ ። በዚህ ቀን ከይማም ጋር የነበረው ጦር ፳፻፳ ፈረሰኛ ፲፪ሺ የእግረኛ ጦር ነበር ። በግራ የሱማሌ የሀርቲ የማይት ባለሰይፍ ጦር ፫፻ . . . . . ። እንደዚሁም የይበሪ ነገድ ፬፻ ባለቀስተኛ ጦር እነዚህን ለግምባር ቀደሙ ፳፻ ፈረሰኛ ጦር ጨመረና ሥፍራችሁን አጠንክራችሁ ያዙ ፣ ከመካከላችሁ አንድም ጦረኛ አይራቅ ብሎ አዘዘ . . . . . . ። ሀምዛህ ኤል ጁፊ የሚባለው ክርስቲያኖቹን ሲያይ በፍጹም ራሱን መቆጣጠር ስለማይችልና እንዳበደ ግመል ስለሚቅበጠበጥ ሁለት ሰዎች አጥብቀው ይዘውት ነበር ። ለውጊያ ከፍ ያለ ሕመም ነበረው ። የሀርቲም አገር ሰዎች በሙሉ እንደርሱ ተቅበጥብጠው ነበሩና የቀሩት ቆዩ ክርስቲያኖቹ ወደኛ ጠጋ ይበሉ እያሉ ይጋብዟቸው ነበር ። አብደላ የሚባለው የአዋቂ ጻድቅ (ናዝራዊ ብጤ) ከተቀመጠበት በቅሎ ወርዶ ጋሻውን ከአነገበና ሰይፉን መዞ ከያዘ በኋላ ወደ መሬት ተደፍቶ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ . . . . . ።

ክርስቲያኖችም በሰባት ረድፍ ጦራቸውን አሰልፈው ወደኛ ይጓዙ ነበር ፣ የሀበሻው ንጉሥ ወናግ ሰገድ ከጦሩ በስተኋላ ሆኖ ያዘምት ነበር ። እርሱንም የሚጠብቁ ዘበኞች ፬፻ በቀኝ ፬፻ በግራ ነበሩትና በዚህ ቀን በየጦሩ ውስጥ ገብተው እንዲዋጉ ከፋፍሏቸው ነበር ። የደለበውን የጦር መሣሪያ ፣ የዳዊት ጥሩር ፣ የግብፃውያን ሰይፍ የካትን (ሕንድ) ጦር አውጥቶ ለየወታደሩ አድሎት ነበር ። የፈረሰኛውም ጦር የማይቆጠር ነው ። በዚያን ጊዜ የያንዳንዱ የክርስቲያኖቹ ሰልፈኛ ወታደር የእስላሞችን አምስት ጊዜ ያህል ነበር ፣ ይህም ምሳሌው በአንድ ጥቁር ኮርማ በሬ ገላ ላይ ነጭ እንደፈነጠቀበት ዓይነት ነበር ። በዚያን ጊዜ ይማም አህመድ "የልዑል እግዚአብሔርን ስም አንሡ እነሱን (ክርስቲያኖቹን) አትመልከቱ በነርሱ ላይ የእግዚአብሔርን ተራዳኢነት ለምኑ በርቱ ጽኑ እግዚአብሐር ከናንተ ጋር ነው" ብሎ ለእስላሞቹ ተናገረ . . . . . አሁን ተዋጊው ሰልፈኛ እየተጠጋ ፣ ጦሮች ወደፊት አፈጠጡ ። ካህኑ አቡበከር እግራኝ ሰንደቅ ዓላማ ሥር ሆኖ እስላሞቹን ለውጊያ በመለመን እንደዚህ እያለ የተናገረው ዲስኩር የሰውን ልብ ሁሉ ቀሰቀሰው ፣ ዓይኖ

(3) ቁራን ሱራት 57. 5 ቍጥር 2

ቹንም በእንባ አራሰ፡ "የእስላም ሠራዊት መንግሥተ ሰማያት ያበራል፥ ገሀነመ እሳት ተዘግቷል ፤ መላእክት ከላይ ከሰማይ ቁልቁል ይመለከቷችኋል ። ዓይናቸው የጠቋቆረው ቆንገኆች ሴቶች (ሁሪ) ሊቀበሏችሁ አጊጠዋል ። በዘለዓለማዊው ሕይወት ደስ ይበላችሁ ።"

በዚህ ዓይነት ከቁራን ላይ በመጥቀስ ስለሃይማኖቱ ሲዋጋ የሚሞተውን እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ብርሃኑን አብርቶ ቆንገኆቱን አዘጋጅቶ እንደሚጠብቀው ከማስረዳት ጋር ልብን በሚነካ ልዩ ልዩ አነጋገር አህመድ ግራኝና ዋናው መምህር አቡበከር አርሹናህ የተዋጊውን ልብ ደህና አድርገው አዘጋጁት ። በዚህም ዓይነት የተዘጋጀው ጦር ሠራዊት ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው ከሚመሩት ሠራዊት ጋር በሽምብራ ኰሬ ተዋግቶ ማሸነፉን እነሆ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከት ።

## ምዕራፍ ፴፱

## በሽምብራ ኰሬ ዓፄ ልብነ ድንግልና ግራኝ አህመድ ያደረጉት ውጊያና የንጉሠ ነገሥቱ መሸነፍ (፲፭፻፴፩ ዓ. ም. መጋቢት ፲፩ ቀን)

የዓረቡ ጸሐፊ ዓረብ ፋቂህ በዚያው በጦርነቱ ሰዓት ከሥፍራውና ከሰልፉ ውስጥ ተገኝቶ የጻፈው ወደ ዘመናችን ተላልፎ ልናነበው ስለቻልን በግራኝ አህመድ የጦር ማንባር ያለውን ዝግጅት በሰፊው ለመረዳት ቻልን ። የውጊያውን አገርማመሩንም ፍጻሜውንም እነሆ ልናነብ ነው ። ዳሩ ግን በሚያሳዝን ረገድ በክርስቲያኖቹ በኩል ያለው ወታደራዊ ድርጅት ከነጦርነቱ በኛ ጸሐፊዎች እጅ ተዘጋጅቶ ወደ ዘመናችን የተላለፈ ጽሑፍ ባለመኖሩ በትክክል ሁኔታውን ለመገመትና ለማመዛዘን አልቻልንም ። የደረጃ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለበት በኩል የሥን ጽሑፍ ድርጅት ጠፍቶ ዓባይ ገነን ሆኖ በተነጋው በግራኝ በኩል ይኸን የመሰለ ዝርዝር ታሪክ ሲገኝበት ከዚህ በፊት እንዳልነው ሥነ ጽሑፍ በማደራጀት ረገድ እስላሞቹ በተለይ ዓረቦቹ ይበልጡናል ብለን ለማመን እንገደዳለን ። የግራኝ ጦርነት ጽሑፉን አጠፋው እንዳንል ግራኝ ከሞተ በኋላ ለምን አልተጻፈም የሚል ጥያቄ ሲመጣም ለመልሱ በቂ ምክንያት የለም ። እንዲያውም የጦርነት ታሪክ የሚጻፈው በጦርነቱ ፍጻሜ ላይ ነው ። ስለዚህ የአጻጻፍ አቅማችን ያው በዚህ መጽሐፍ በመገርመሪያው ክፍል ላይ ከአመለከትነው የዝቅተኛና የቁንጽል ደረጃ ሊያልፍ አይችልም።

ይሁን እንጂ ተጽፎ ባናገኘውም በኛም በኩል የጦሩ ድርጅት በየመልኩ ተሰልፎ መቅረቡን በሰባት ረድፍ ተሰልፎ ውጊያ መገርመሩን ዓረብ ፋቂህ ጠቅሶታል ። ተዋጊውንም ጦር በርታ ላገርህና ለንጉሥህ ለሃይማኖትህ ብትሞት መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ የሚል ልብ የሚያጸና መንፈስን የሚያበረታ ንግግር ከመንፈሳዊ አባቶች እንደበት እንደሚነገር ባይጻፍም የታወቀ ነው ።

ዳሩ ግን የኛዎቹ በልበ ሙሉነትና በመዝናናት ለድሉ ሳይጠራጠሩ ሲዋጉ ግራ

ኝና ጦሩ ግን ራሳቸውን በአምላክ ፊት አዋርደው በሞትና በሽረት መካከል ሥጋ ትና ቆራጥነት በተበረዘበት የጋለ መንፈስ ስለተዋጉ በቁጥር የሚያንሱት እስላሞች በቁጥር የሚበዛውን ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው አዝማች የሆኑበትን ጦር ለማሸነፍ ሲችሉ ጩካኝና ጭስ መውጫ አያጣም የተባለው ተረት ለግራኝ በዚህ ዓመት በዚህ ቀን እንደተአምራት ተፈጽሞለታል ።

በኛ በኩል ያለውን መዝናናት የሚያስረዳን ውጊያው ሊጀመር ሲል ንጉሠ ነገሥቱ «እንዳያመልጧችሁ ያዟቸው» ያሉት ነው ። ይኸን የጻፈ ዓረብ ፋቂህ ነው ። እውነት ከሆነ የንጉሡ ሥጋት ለመሸነፉ ሳይሆን እስላሞቹ ከተሸነፉ በኋላ ሳይሞቱ ወይም ሳይማረኩ አምልጠው ወዳገራቸው እንዳይመለሱ ነው ማለት ነው ። ከዚህም እያይዞ የዓረቡ ጸሐፊ ከድሉ በኋላ የእስላሞቹ ምርኮኞች የሚታሠሩበት ብዙ ገመድ ንጉሡ አሲዘው እንደነበረ ያመለክታል ።

የባደቁና የሽምብራ ኵሬ የጦርነት ምዕራፍ ባንድነት በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ ከ፲፰ ገጽ በላይ ሥፍራ ሲይዝ በኛ ታሪክ ነገሥት ዘንድ ስለ ሁለቱም ጦርነት በግዕዝኛ የተጻፈው ጽሑፍ ፺ መስመር አይሞላም ። ቃሉም ወደ አማርኛ ሲተረጐም ባጭሩ እንደዚህ የሚል ነው ።

«ደገልሃን በተሸነፈ በ፪ኛው ዓመት ልብነ ድንግል በነገሠ በ፳፩ኛው ዘመነ መንግሥታቸው ሰመርማ (1) ድረስ ግራኝ መጥቶ ከንጉሡና ከሠራዊታቸው ጋር ተዋግቶ እስከ ከተማቸው እስከ ሽምብራ ኵሬ ድረስ አባረራቸው ። በዚያም በመጋቢት ፲፩ ቀን (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) ተዋግተው ብዙ መኳንንት አለቁ ። ጎዱግ ራስ ማኅፀንቶ ፣ የሸዋው ገብረ መድኅን ፣ ራስ ዓምዱ ፣ ጸሐፊ ላም ሮቢል ፣ አሴር ሌሎቹም ብዙዎች ሞቱ (2) ።

ISIC

መቼም የቦታና የወረዳ ስም ብዙ ጊዜ በኛ ታሪክ ነገሥትና በዓረብ ፋቂህ ዘንድ የሚጠቀሰውን ማዛመድ የዓረቡ ጸሐፊ የሚጠቅሳቸውን የቦታና የወረዳ ስሞች ሁሉ በዛሬው የኢትዮጵያ ወረዳዎች ውስጥ እያገናኙ ለአንባቢ ማብራራቱ ችግር መሆኑን ጠቅሰናል ። አሁንም ዓረብ ፋቂህ ባደቁ የሚለው ግዕዙ ሰመርማ የሚለው ሁለቱም ከተስማሙበት ከሽምብራ ኩሬ ጋር በዚሁ ያን ጊዜ ፈጠጋር በሚባለው ዛሬ የየረርና ከረዩ አውራጃ በተባለው ግዛት ውስጥ ሆኖ በዝቋላና በሞጆ ወንዝ አጠገብ መሆኑን የዓረቡ ጸሐፊ አነጋገር ያስረዳል ። ሽምብራ ኵሬን

(1) የዛሬው የዱከም ወንዝ ያን ጊዜ ከጋላ ስራት በፊት ሰመርማ ይባል ይሆን ?

(2) ወእምዝ በ፪ ዓመት (ደጋልሃን በተሸነፈ) ወበ፳ወ፩ ዓመተ መንግሥቱ ለልብነ ድንግል ንጉሥ መጽአ ግራኝ እስከ ሰመርማ ወተፃብኦ ንጉሥ ምስለ ሠራዊቱ ወሰደዶ እስከ ሽምብራ ኵሬ መዲናቲሁ ለንጉሥ ። ወገብሩ ፀብዓ በሕየ አመ፲ወ፩ ለመጋቢት ወኅልቁ ብዙኃን መኳንንት ወሞቱ እለ ጎዱግ ራስ ማኅፀንቶ ፣ ወገብረ መድኅን ፣ ሸዋ ራስ ዓምዱ ፣ ጸሐፊ ላም ሮቢል ፣ ወአሴር ወካልኣን ብዙኃን ። ታሪክ ነገሥት ፓሪስ በ143 ቍጥር የተቀመጠው ገጽ 92 (በስሕተት የጦርነቱን ቀን መጋቢት ፳፩ ቀን ብሎታል) ። Etudes Sur l'histoire d'Ethiopie-Rene-Basset ገጽ 327

"መዲናው ለንጉሥ — የንጉሥ ከተማ" ሲል በርግጥ ዓፄ ልብነ ድንግል የረር አጠገብ አንድ ከተማ እንደነበራቸው ብዙ ጊዜ በቃል ጭምር ሲነገር ኖሯል ።

ነገር ግን ንጉሡ የተዋጉት እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ አንድ ጊዜ ያውም ባንድ ቀን ሽምብራ ኩሬ ሲሆን ታሪከ ነገሥታችን መጀመሪያ ስመርማ ላይ ተዋግተው ሳይሆንላቸው ቀርቶ ወደ ከተማቸው ወደ ሽምብራ ኩሬ መጥተው ተዋግተው ብዙ መኳንንት እንዳለቀባቸው ያሳያል ። ምናልባት የባደቁሙን እነአውራይ ኡስማን፥ እነራስ ማኅፀንቶ ያሉበትን ያው ራሳቸው እንዳሉበት ቆጥሮት ይሆናል ።

ሽምብራ ኩሬ የሚባል ከተማ ዛሬ በዱከምና በጠቅላላው በናዝሬትና በቢሾፍቱ ውስጥ አለመኖሩን ተረድቻለሁ ። ነገር ግን ቢሾፍቱ አጠገብ ያለው የጨለቅለቃ ኩሬ በሸሸበት ጊዜ ሽምብራ ዛሬም ይዘራበታልና እርሱ ይሆናል የሚል ግምት አለ ። ስለዚህ ግራኝ በመጀመሪያ ዱከም አቅራቢያ ተዋግቶ አሸንፎ ከዚያ እስከ ዛሬው ጨለቅለቃ (ሽምብራ ኩሬ) ድረስ አሳዶ ከዚያ ላይ ታላቅ ጦርነት አድርገው ይሆናል ። በዚህ ዓይነት ይህ ታላቅ ጦርነት የተደረገበት የሽምብራ ኩሬ የዚያን ጊዜ ከተማ ጋሎች ከገቡበት ወዲህ ዛሬ ቢሾፍቱ (ደብረ ዘይት) ከሚባለው ከጨለቅለቃ ኩሬ አጠገብ ይሆናል ። ይኸውም ግምት እንጂ የተጣራ አይደለም ። በሸንኩራም ውስጥ ሽምብራ ኩሬ የሚባል አለ ይባላል ። ነገር ግን ወደዚያ ሊሆን አይችልም ።

የሆነ ሆኖ ንጉሡ ፲፭፻፴ቱ ከአማራ አገር ይዘው የመጡት አዲስ ጦርና በባደቁ የነበረው ተደባልቆ ለጦርነቱ ከተደረጀ በኋላ የግራኝም ጦር ከባደቁው ጦርነት ወዲህ ባጠገቡ ያለው ምናልባት አዲስ የመጣለትም ጦር ባንድነት በተሰለፈና የሁለቱ የክርስቲያንና የእስላም ጦር ከተቀራረበ በኋላ ከመዋጋት በቀር የቀረው ነገር የለም ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ ካደረጋቸው ከ፲፭ ዓመት ጦርነቶች ሁሉ ዋነኛውንና ንጉሡ ነገሥቱ ጠቅላይ አዝማች ሆነው የተዋጉበትን የዚህን ጦርነት አዠማመሩንና አፈጻጸሙን ግዕዝኛው ባጭሩ ጠቅሶ ያለፈውን ከዚሁ ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ዝርዝሩን ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«በዚያን ጊዜ እስላሞቹ "እንግዲህ ሮጠን ክርስቲያኖቹን እንግጠማቸው" ብለው ይማምን ጠየቁት እርሱ ግን "እነርሱ ሲወጉዋችሁ ተቀበሉ እንጂ እናንተ አትገፉ" ሲል ከለከለና ይልቅስ "ሥፍራችሁን አጠንክራችሁ ያዙ ጦራችሁን ደግኑ ቢጋሻችሁ ሰውነታችሁን ከልሉ የእግዚአብሔርን ስም ሳታነሡ አንድም እርምጃ አትራመዱ ። እስላም ሆይ ድልን የሚያገኙ ታጋሾች ጽኑዎች መሆናቸውን፥ ፈሪና ልል ወራዳ ተሸናፊ መሆኑን እወቁ ። ጽኑውን እግዚአብሔር ይረዳዋል ዛሬ ከኛ ጋራ የሰይፍን ውጊያ ታግሦ የጸና ነገ ከኛ ጋር ደስ ይለዋል ። ከዚያ ወዲያ ድካም የለበትም . . . . ." እያለ እየደጋገመ ሲናገር ክርስቲያኖቹ ሥፍራቸውን ለቀው ለውጊያ ብዙ ሆነው ሰይፋቸውን እያብለጨለጩ ሲመጡ እስላሞቹ አዩዋቸው ። ንጉሡ ወናግ ሰገድ . . . . . . "ተዋጉ" የሚል ትእዛዝ ሲሰጥ እንዳንድ ሰው ሆነው ከእስላም ጦር ከቀኙ ዘማች ጋር ገጠሙና ይወጉዋቸው ገገመር ። እስላሞቹም ጸን

ው ያዙ ። እንደዚሁም የክርስቲያኖቹ የቀኝ ዘማች ከእስላሞቹ ከግራው የሱማሌ ዘማች ጋር ተጋጠመ ። የትግሬ ጦር ከንሹማምንቱ ይማም ያለበትን መካከለኛውን ሰፍገሥግሶ ይዞ ይዋጋ ዠመር ። ይማምና ጓደኞቹም የእስላምነት ልባቸውን አጠንክረው ተቀበልዋቸው ። የጦር ሠራዊት ተደበላለቁ ፤ ሰይፎች ተመዘዙ ፤ ጦሮች ተገተሩ ፤ መለዮና የጦር ምልክት ተሰቀሉ ሰንደቅ ዓላማዎች በአየር ላይ ነውለበለቡ ። ልጓም ከልጓም ተጋጨ ። ፈረሶች ጮኹ (አስካኩ) ። ትልቅ አቧራ ተነሣ ። ከመሣሪያው ክብደት የተነሣ በተዋጊው ደረት ላይ ላብ ተንቆረቆረ ። ይበ ጾተ ጊዜ ድምጡ እያስተጋባ የሚሰማ የሁለቱም ጦር ሠራዊት የሰውና የፈረስ ጩኸት ልጓምና ልጓም እየጋጨ ሰይፍና ጋሻ እርስ በርሱ ተደባልቆ ሲራኮት በዚህ መካከል አንድ ተናጋሪ "የመሐመድ ወገኖች ትንሽ በርቱ ብዙ ታገኛላችሁ ፤ ዓይ ናቸው የጠቆረው ቆንገዦሮች ሴቶች (ሁሪ) በሰይፋችሁ ጥላና በጦራችሁ ጫፍ ናቸው" ብሎ ጮኾ ተናገረ (1) ።

ይማም አህመድና ጓደኞቹ ጠንክረው ያዙ ። ከዚያ ደግሞ ይማም የክርስቲያኖቹ ጦር በዝቶ ወደሚዋጋበት ወገን ዘሎ ሄደና ብዙ ሰው ጨረሰ ። የድሉ ሰንደቅ ዓላማ ከራሱ በላይ ይውለበለብ ነበር ። በግራ በኩል የሱማሌው ተዋጊ ግን ጦርነቱ መበርታቱን ሲያይ ሸሽት ዠመረ ። ክርስቲያኖቹም እየተከታተሉ ብዙ ፈጁላ ቸው ። ብዙም ማረኩ ። የሞቱት ፫ሺ ይደርሳሉ ። አለቆቻቸው የይማም አማች ማታን ቤን ኡስማንና ሌሎቹም እንአህመድ ገራድ ፤ ቜፀሮሊ ገራድ የማታን ወን ድም . . . . . በጉብዝና ተዋጉ ። እነሱም ጓደኞቻቸው ትተዋቸው ሲሸሹ ወደ ይማም መጥተው በፊቱ ተዋጉ ። የሀርላሀ ነገዶች በሚዋጉበት በቀኙ መሥመር የመዠመሪያው የሁለተኛውና የሦስተኛው ረድፍ የክርስቲያን ጦር እየተከታተለ ወጋቸው ። ጦርነቱም እንደወፍጮ ድንጋይ ይዞር ዠመር ። የተዋጊዎቹም ጭንቅላት ተደበደበ ፤ ሀበሾቹም በቀኙ የእስላም ዘማች ላይ ጸንተው ተዋጉ ፤ እነሱም በሚያስ ደንቅ አኳኋን ተከላከሉ ። ሌላ አዲስ የክርስቲያኖች ጦር እየተጨመረ ስለወጋቸው እያፈገፈጉ የይማም ሰንደቅ ዓላማ እስከሚገኝበት እስከ መካከል ድረስ መጡ ። እዚያ ላይ ታላቅ ውጊያ ተደረገ ። የባሕር ወታደሮች (2) የፈረሶቻቸው ቅልጥም እስኪታጠፍ (በድካም) ወፍራም አቧራ ቆሞ እስኪሄድ ድረስ በኃይል ተዋጉ ። እስ ላሙም ክርስቲያኑም ጓደኛውን አያውቅም ፤ ወንድም ወንድሙን አያይም ነበር ። ሀበሾቹ በሚያባርሩዋቸው እስላሞች ላይ እስኪወድቁ ድረስ ጦርነቱ ዘገየ ። በብዙ ሺ የሚቆጠር ሰው ሞተ ። መሬቱ በሰው ሬሳ ተሸፈነ ። በሁለቱም ወገን ቁስለኛው በረከተ ይልቁንም በክርስቲያኖቹ ዘንድ . . . . . ጦርነቱ ከጧት ዠምሮ እስከ አስር ጸሎት (የማታ ያስር ሰዓት ጸሎት ?) ድረስ ቆየ ። በዚያን ጊዜ እስላሞች የእግ ዚአብሔርን ታላቅነትና አንድነት እያነሡ ጮኹ ለመሐመድም . . . . . ሰላምታ

(1) የኛ ወንጌል አንድ ወንድ ላንድ ሴት ያዛል ማቴዎስ ምዕ. 19 ቍጥር 5-6 ። በሰማይ መጋባት የለም ማቴ. 22 ቍጥር 30 ። ቁራን ግን በምድር ብዙ ሚስት እንደሚፈቅድ በሰማይም ጻድቃን በነት ከቆንጆ ዠርት ጋር እንደሚጋቡ ያረጋግጣል ። ሱራት 44 ቍ. 54

(2) የባሕር ወታደሮች ሲል ከቀይ ባሕር ማዶ ለእርዳታ የመጡትን ቱርኮች ዓረቦች ወይም ፋርሶችና ሕንዶች ሲል ነው ።

አቀረቡ ። እግዚአብሔርም ድልን ሰጣቸው በጠላቶቻቸውም ልብ ፍርሃትን አሳ ድሮ እንዲሸሹ አደረጋቸው . . . . . ።

በዚህ ቀን ጦርነት ብዙ የክርስቲያን የጦር አለቆች ሞቱ ። ከነዚሁ ውስጥ አዝ ማች (ጸሐፊ ላም) ሮቤል በይማም አሽከር በአረዱ እጅ ሞተ ። እግባ (ዕቁበ) ሚካ ኤል የሚባለው ጉበዙና አስፈሪው የሮቢል ታናሽ ወንድም ይማም ራሱ በጦር ያረ ቱን ቢወጋው የጦሩ ጫፍ በጀርባው ወጥቶ ሞተ . . . . . ፤ ሁለት የንጉሡ ግምጃ ቤቶች ስማቸው ጃውሂርና መንዲል የሚባሉ ሁለተም የንጉሡን ባንዲራ በራሳ ቸው ይዘው ነበር ። ክርስቲያኖቹ እንደ ንጉሡ አድርገው ይገምቷቸዋል (1) ጃውሄ ርን የገደለው ኤሚር መሐመድ የኤሚር መሐመድ ቤን ዘሀርቡይ ኡስማን ልጅ ፤ መንዲልን የገደለው ድል ሰገድ የሚባል የሲም ፈረሰኛ ፤ የሲሬን (ሸሬ) ሹም ራገድ ዲን ገደለው ። ለንጉሡ በናቱ በኩል የሚዛመደውን ትልቁ አዝማች ዮናኤል የሚባ ለውን ገራድ ሻሙን እጁን ቀረጠው ፤ ከኋላውም አብይ ኢን ናስር በጦር ወግቶት ነበር ። ነገር ግን አምልጦ ሄደ ። ኡስማን ሺክ ግርን በለው ራብ ከሚባለው ጥሩር ከለበሰው ጋር ተማታና ኡስማን ጥሩሩን በሰይፍ ሲመታው ግማሹ እሰውነቱ ላይ ቀርቶ ገሚሱ ተቆርጦ እመሬት ላይ ወደቀ ። የጸለምትን ሹም አንድ እስላም ገደ ለው ፤ አዝማች ገብረ መድኅንን አንድ ጥርስ የሌለው እውማይደይህ ገደለው ። አዝ ማች ዘመንጃ የሚባለውን የወሰን ሰገድን ዘመድ ወዚር አዶሌ ገደለው ። አዝማች (ሕዱግ ራስ) ማኅፀንቶን፲፰፻፸፫ድ የቀስተኞች አለቃ የሆነ እዳም የሚባል ሱማሌ ገደለው ። አዝማች ዋጋሙሀ በተክላይ እጅ ፤ ባሕር ነጋሽ ዘወንጌል የድሆና ጌታ በአብድር አዛክ ቤን ሰሃል እጅ ተገደለ ። የአጋሚ ፤ የሸጋሬ (ወገሬ) ሹም የተምቤን ሹም የአበርጋሌ ሹም ሞቱ ። አዝማች (ራስ) ዓምዱ በአንድ እዳሙ በሚባል የእስ ላም የእግረኛ ወታደር እጅ ተገደለ ። የሞቱት የትግሬ ሹማምንት ብቻ ቍጥራ ቸው ፹፮ የተራው የትግሬ ወታደር ፲ሺ ይደርሳል ። ፩፻፹፭ የሌላ አውራጃ ሹማም ንት በዚሁ ቀን ጦርነት ሞቱ ። እነዚህም እያንዳንዳቸው ፩ሺ ፈረሰኛ ሌላው ፭፻እንዱ ፮፻ ወታደር የየራሳቸው ጭፍራ ነበራቸው ። ፈረሰኛ ተደባልቆ በሚዋጋበት ጊዜ እስላሞቹ ፮፻ የክርስቲያኖችን የፈረስ ቋንጃ በሰይፍ ቆረጡ ።

ከእስላሞች ወገን የሞቱት ሀምዛህ ኤል ጁፊ ፤ ሀዲድ (ጀዲድ) ኮርጁሀ ፤ ኢብ ራሂም . . . . . ፤ የሲም ወገን ሕግ አዋቂና ሰባኪው መሐመድ ፤ ዳሉ ባሊ ፤ መሐ መድ ደዋሮ ናቸው ። የሞተው የሱማሌ ፤ የሀርላህ ፤ የመለሳይ ፤ የዓረብ ወታደር ቍጥር ፭ሺ ይደርሳል ።

ቍጥር ሥፍር የሌለው መሣሪያና ዕቃ ፈረስ ፤ ጥሩር ፤ ሰይፍ ፤ ጦር እስላሞቹ ማረኩ ። አንድ የንጉሡ አማች የሆነ ትልቅ ሰው ስሙ ተክለ መድኅን የሚባል ተማ ርኮ ወደ እስላም አገር ከሄደ በኋላ ወገኖቹ ፳፻ ወቄት ወርቅ ከፍለው አስመለሱት ። ስለዚህም ይማም አሕመድ ይኸን አሸናፊነት ከአገኘ ወዲህ በደስታ በክብር ተመ ልሶ በራጅብ ወደ አገሩ ወደ ሐረር ገባ ። ወደ ሐረር ከመመለሱ በፊት ይኸን (የሽ

(1) ሊቃነ መኳሶቹ መሆን አለባቸው ።

ምብራ ኩሬ) ድል ወዲያው እንዳገኘ ባጠገቡ ላሉት የእስላም ሹማምንት "ዛሬ
እግዚአብሔር እኛን ረድቶ ጠላቶቻችንን አዋረደ ፤ አሁን የንጉሡ ከተማ ወደ ሆነ
ችው ወደ ባደቄ እንሂድና እናፈራርሳት ባገራቱም በኢትዮጵያ ተቀምጠን እየመ
ታን እየተዋጋን ጠላቶቻችንን እናድክማቸው" ቢላቸው ሹማምንቱ እንደዚህ
ሲሉ መለሱ "የእስላሞች ይማም ሆይ የደረሰብንን ሁሉ አታይምን እነሆ ብዙ ወታ
ደሮቻችን ሞቱ ፤ እኛም በቁስል ተሸፍነናል ፤ ያለን ስንቅ ትንሽ ነው ። አሁን ይበ
ቃናልና ወደ አገራችን ተመልሰን ፤ አገራችን አርፈን እንደገና ወታደሮቻችንን
አደራጅተን ሁለተኛ መጥተን እንዋጋለን ። ቀርተን እንዋጋለን ብለህ ከዘዝኸን
ግን ካንተ ጋር እንቀራለን" የዚህን መልስ ሲሰማ ይማም አህመድ እሺ ብሎ ከሹማ
ምንቱና ከጦሩ ጋር ተመልሶ ሐረር ገባ ። በዚያም የሻባንን ፤ የረመዳንን በዓል ውሎ
እስከ ሻውል ድረስ (ሚያዝያ ፤ ግንቦት ፤ ሰኔ አጋማሽ) ቆየ» (1) ።

የሽምብራ ኩሬን ጦርነት እነሆ ዓረብ ፋቂህ በዚህ ዓይነት እየተረከ ይጨር
ሳል ። ይህ ጦርነት የተደረገበት ዘመን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር መጋቢት ፲፭
ቀን ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. መሆኑን ግዕዝኛው ታሪከ ነገሥት ቀደም አድርጎ አረጋግጧል ።

በዚህ ስመጥሩ በሆነው በሽምብራ ኩሬ የጦርነት አውድማ የግራኝ ጦር ባዔ
ልብነ ድንግል ጦር ላይ አሸናፊነትን ማግኘቱ በጠቅላላ አገሪቱን ወደፊት ለመግ
ዛት ታላቅ ዕድል አቀርቦለታል ። ይሁን እንጂ ዓፄ ልብነ ድንግል ገና ያልተሸነፈ
ጦር በባሌ በደዋሮ በፈጠጋር አላቸው ። በዚህ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ንጉሡ ተሸ
ነፉ ፤ ግራኝ አሸነፈ ቢባልም የተጋጠመው ጦር የተለያየበትን ሁኔታ ለመግለጽ
ነው እንጂ አሸናፊው የግራኝ ጦር ተሸናፊውን የንጉሡን ጦር እንኳን እስከ መጨ
ረሻ ማባረር ይቅርና እንዳረብ ፋቂህ አጻጻፍ (2) ለጦርነቱ ቦታ ቅርብ የሆነውን የባ
ደቄን ከተማ እንኳን የግራኝ ጦር ለመያዝም ለማፍረስም አልቻለም ። የባደቄን
ከተማ ዘርፎ ያፈራረሰው ሐረር ሄዶ ከተመለሰ በኋላ ነው ።

ይኸንንም ከተማ ከማፍረስ ያዳነው ባለፈው ጽሑፍ ላይ እንደተገነዘብነው
የንጉሡ የጦር ወታደር ይልቁንም የትግሬ ሹማምንት ከነጭፍሮቻቸው በእስላሞቹ
ላይ ባደረጉት ጉዳት የተነሣ ሹማምንቱ ከሽምብራ ኩሬ ድል በኋላም ጦርነቱን
ለመቀጠል ባለመቻላቸው ነው ። የሆነ ሆኖ ባለፈው ሁሉ እንዳነበብነው ድል
ባገኘ ቍጥር እርሱ እንቀጥል ሲል ወታደሩ አገራችን ሄደን አርፈን እንመለስ
እያለ አሳቡን ቢያሰናክልበትም ወታደሩን ለማስደሰት ሐረርጌ ሄዶ ካረፈ በኋላ
ተመልሶ ያው መዋጋቱም ማሸነፉም በምንም ዓይነት አላቋረጠም ። ንጉሡ ነገ
ሥቱ ያዘመቱትን ቍጥሩ ከፍ ያለውን የጦር ሠራዊት ያሸነፈው ግራኝ ወደፊት
በግናቸውም የጦር አለቃና ጦር ፊት ሊሸነፍ አይችልም ።

ባለፈው እንደተመለከትነው ግራኝ አህመድና ሰባኪው ሊቅ ሲዲ አቡበከር
የበረከተውን የሱማሌ የአዳል ነገድ ከባሕር ማዶ ለእርዳታ የመጡትን ጭምር ባን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 120 - 131
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 131

ድነት ለዚህ ጦርነት እንዲያብሩ ከማድረጋቸውም በቀር በውጊያ ሰዓት ድልን የሚያስገኘው ዋነኛው ጉዳይ ጸንቶ በርትቶ ውጊያውን መቀጠል መሆኑን በየጊዜው ተዋጊው ጦር የሚያምንበትን የቀራንን ቃል እየጠቀሱ ከልቡ የሚመኘውን መንግሥት ሰማያትንና በዚያ የሚገኙትን ቆነጃጅት ተስፋ እያስደረጉ በመንፈሳዊም በሥጋዊም ምክር እንደውታል ። እንኳን ከውጊያው በፊት ሁለቱ የጠላት ወታደሮች እግረኛው ከእግረኛ ፈረሰኛው ከፈረሰኛ ተደባልቆ በሚከታከትበት ሰዓት አንደበተኛው የእስላም ተናጋሪ «የመሐመድ ወገኖች ትንሽ በርቱ ብዙ ታገኛላችሁ ዓይናቸው የጠቆረው (የተኳለው) ቆንጆ ሸርት ሴቶች በሰይፋችሁ ጥላና በጦራችሁ ጫፍ ናቸው» ብሎ እየጮኸ በመናገር በተፋፋመው ውጊያ ላይ ተዋጊዎቹን ለውጊያ እንዳጸናቸው እንብበናል ። ይኸን የመሰለው አነጋገርና የሰማያዊ ኑሮ ተስፋ ለዚያን ዘመን ተዋጊ ወታደር ሊሸነፍ ለቀረበውም ቢሆን አዲስ የተዋጊነት መንፈስ ቀስቅሶ ሰማዕትነትን ያስመኘዋል ።

በክርስቲያኖቹ ወገን ያሉት መንፈሳውያን አበው ንጉሡም ራሳቸው ይህን በመሳሰለ ክርስቲያናዊና ወንጌላዊ ቃል በውጊያው መካከል ወዲያና ወዲህ እያሉ የተዋጊውን ወታደር መንፈስ አነቃቅተውት እንደሆነ አናውቅም ። ያለዚያ እስላሞቹ ባደረጉት ትንሽ ብርታት ላይ ቍጥራቸው የበረከተው ክርስቲያኖቹ ደግሞ በበኩላቸው ትንሽ ጽናት ጨምረው ቢሆን ኖሮ ከወታደር ብዛት ጋር ከቀድሞ ከነዓምደ ጽዮን ዝምሮ በእጃቸው የቆየው የድል አድራጊነቱ ዋንጫ አሁንም ከነሱ እጅ ሊወጣ ባልቻለ ነበር ።

ዳሩ ግን የግራኝ አህመድና ያፄ ልብነ ድንግል የመሪነት ዓይነቱና መልኩ ለየቅሉ መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ታሪከ ነገሥቱ ራሱ ባንዳንድ ቦታ እንደሚያስረዳን ዓፄ ልብነ ድንግል ጊዜአቸውን ሁሉ በታላቅነትና በከፍተኛ ደረጃ ከድልወትና ከልስላሴ ጋር መንፈሳዊ መጽሐፍ በማንበብ ወይም ስለመጽሐፍና ስለቀለም ጉዳይ ከሊቃውንት ጋር በመነጋገር ሲያሳልፉ የኖሩ ከወታደርነት ይልቅ መንፈሳዊነት ወደተጫነው ወደ ቀለም ሰውነት ያዘነበሉ ሲሆኑ ባላጋራቸው ግራኝ አህመድ ግን ከቀለም ሰውነት ይልቅ ራሱ የተዋጊነትና ያዋጊነት መንፈስ የሞላው የእስላሞቹን ተጠቂነት የክርስቲያኖቹን አጥቂነት ለመበቀል ከሚበቱ ከድልወንበራና ከሹማምንቱ ጋር ከልብ ቆርጦ የተነሣ ባገሩ ውስጥ ከነአቡበክር ሱልጣን ጋር ባገር ውጭ ከክርስቲያኖቹ ከነፋኑኤል ከነደገልሃን ጋር ያለዕረፍት እየተዋጋ ሰውነቱን ለችግርና ለጦርነት ያስለመደ ፤ በተድላና በድልወት ሰውነቱን ያላቀማጠለ ክብርን ሥልጣንን ግዛትን ገና ያልጠገበ ፤ ምኞቱን ገና ወደፍጻሜ ያላደረሰ እፍላ የጦር መሪ ራሱ ጦራጦራ ተዋጊ ስለሆነ እንደዚህ የመሰለ ልዩነት በሁለት መሪዎች መካከል ሲገኝ ሁልጊዜ የድል አዝማሚያውና ዝንባሌው እፍላና ፈቃደኛ ፤ ደፋርና ወጣት ወደ ሆነው ወገን ነው ። እስክንድርም ናፖሌዎንም ዓምደ ጽዮንም ቴዎድሮስም ወደ ድል ጕዳና የተጓዙበት የጦርነት ጥርጊያው መንገድ ይኸን የመሰለው ነው ። በተለይ በዚያን ዘመን ካገር ይልቅ ለመሪ ዋጋ በሚሰጥበት ዘመን የመሪ ግንባር ቀደም ተዋጊነት ለድል አብነት ነው ።

የግራኝ አህመድን ዓይነት መንፈስ ጉብዝናና ድፍረት የነበረው አላይ የጠቀስ ነው ንጉሠ ነገሥት ዓምደ ጽዮን ነበር ። ግራኝ አህመድ ባፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (፲፫፻፯ - ፲፫፻፴፯ ዓ. ም.) ተነሥቶ ቢሆን ኖሮ እውነተኛው የመረረ ወይም የከረረ ጦርነት ሆኖ የመጨረሻው እውነተኛ ዝግና ይለይ ነበር ።

እንዳሁኑ እንደ ግራኝ ሳብር አድ ዲን (ሰብረዲን) መሐመድ የይፋትና የአዳል ንና የሱማሌን ነገድ በሙሉ አስነሥቶ በተዋጋ ጊዜ ወጣቱና ዝግናው ዓፄ ዓምደ ጽዮን በእንዴት ያለ አኳኋን በየጦሩ ጐራ ላይ ራሱ እየተገኘ አሸንፎ ከርሱ በፊት የነበሩት ነገሥታት እስከ አልደረሱበት እስከ ሱማሌ አገር ጫፍ ዘልቆ አሳምኖ እን ደተመለሰ ታሪኩን የኢትዮጵያ ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚባለው መጽሐፍ ከገጽ ፩ - ፺፮ ላይ ተዘርዝሮ ይገኛልና አንብቦ ከዚህኛው ጦር ነት ጋር ለማመዛዘን ቀላል ነው ።

ዓፄ ዓምደ ጽዮን ድሉን እስከ መጨረሻ ለማዝለቅ ፤ ጠላቶቹን እስከ ፍጻሜ አሸንፎ ለማስገበር ወደፊት እንግፋ ሲል የጦር አለቆቹ ያለፈን ድል አድራጊነት ንና የወደፊቱን የበረሃ ጉዞ እያመካኙ እንግዲህ ይበቃናል ወዳገራችን እንመለስ ያሉትን አሁንም ግራኝ አህመድ ጦርነቱን እንቀጥል ሲል ሹማምንቱ ይብቃን ወደ አገራችን እንመለስ ከሚሉት ጋር ስናመዛዝነው ያፄ ዓምደ ጽዮንና የግራኝ አህመ ድን የውጊያ ፍቅርና የጉብዝና ተመሳሳይነት ወደ መገንዘብ እንደርሳለን ።

ጦርነቱ ሊዠመር ሲል ግራኝ አህመድ የወታደሩ[illegible]ኔ ሥጋዊና መንፈሳዊ ትግሣፅና ምክር የጦር መላና ዘዴ ጥሩ አድርጎ በተቀመመ አነጋገር እየሞላ የሰበከ ውን መልሰን እናስታውስ «የእግዚአብሔርን ስም ሳታነሡ አንድም እርምጃ ወደ ፊት አትራመዱ ። በጠላቶቻችሁ ላይ የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠይቁ» ሲል ውጊ ያው በጸሎት እንዲዠመር ካደረገ በኋላ ቀጥሎ «ውጊያውን ተቀበሉ እንጂ እናንተ አትዠምሩ ። ዛሬ ከኛ ጋር ታግሦ የተዋጋ ነገ ከኛ ጋር ደስ ይለዋል» ሲል በጸሎቱ ትን የአወጋግ ዘዴ (ታክቲክ) ጭምር እያስተማረ ነው ማለት ነው ።

በዋናው መሪ በግራኝ ንግግር ጐን ሌላው ደግሞ መንፈሳዊው መሪ ካህኑ አቡ በከር አላይ እንዳመለከትነው መንግሥተ ሰማያት ለናንተ ለምትዋጉት ክፍት ነው፤ ገሃነመ እሳት ተዘግቷል ፤ መላእክት ከሰማይ ቁልቁል ይመለከቷችኋል ፤ ዓይናቸው የጠቆረው ቆንዦዥት በዘለዓለማዊው ሕይወት ተጊጠው ይጠብቋችኋል እያለ ሥጋ ለባሲ የሚፈልገውን ተስፋ በመስጠት የሁለቱ የሥጋዊና የመንፈሳዊ መሪ ዎች ንግግር ተባብሮ ተዋጊውን የሱማሌና የአዳል ሕዝብ ፤ ለእርዳታ ከዓረብ ጋር የመጡትን ጭምር መንፈሳቸውን ቀስቅሶ ጠንክረው እንዲዋጉ ድልንም እንዲያ ገኙ አደረጋቸው ። ይኸን የመሰለ አነጋገርና ተስፋ ፈሪንም ሳያበረታ አይቀርም ።

ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ ደግሞ በበኩሉ የውጊያውን ታላቅነት በሁለቱም ወገን ያለውን ጽኑ ግድያ ሲተርክ «ልጓም ከልጓም ሰይፍና ጦር ጐራዴና ጋሻ እርስ በርሱ እየተጋጨ የፈረሶቹ ማስካካት ከወታደሩ ጩኸት ጋር እያስተጋባ አየሩ በአቧራ እስኪሸፈን ድረስ ወታደር እርስ በርሱ ተራኰተ» በሚል በጥሩ የንግግር ቅርጽ ገልጾ ሁኔታው ለጊዜያችን ደርሶ እንዲብራራ ስለአደረገልን ከታሪኩ ጠቃሚነት

በቀር በአጻጻፍ ረገድ ባለ ሙያ መሆኑን ያስረዳል ። ጊዜና አካባቢ ሲያመች ጥሩ መሪ ፤ እንደበቱ የረታ ሰባኪ ፣ በጥሩ ያነጋገር ወዝ ታሪካዊ ጽሑፍን ለማስፈር የሚችል ጸሐፊ ባንድ የዘመን ጊዜ ውስጥ አልፎ አልፎ ያጋጥማል ። አብዛኛ ጊዜ ሦስቱ ሀብት እያንዳንዳቸው ግምታቸው የተለየና ከፍ ያለ ስለሆነ ተደራርበው ላንድ ሰው አይሰጡም ።

## ምዕራፍ ፵

## በሽምብራ ኩሬ የሞቱት የጦር አለቆች ዝርዝር - የውጊያው አመራርና የተዋጊው ወታደር መጠን

በዚህ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት የሞቱትን የጦር አለቆች የኛ ታሪክ ነገሥት የጠቀሳቸውን አምስቱን «እንደዚሁም ብዙዎች ሌሎች» ብሎ ያለፈውን ዓረብ ፋቂህ የግማሾቹን ስማቸውን የቀሩትን የሹመት አገራቸውን እየጠቀሰ ከትግሬ ወገን ፹፯ ከሌሎች አውራጃዎች ፩፻፺፭ በድምሩ ፱፻፵፩ መኳንንት አልቀዋል ያለውን አንብበናል ። ሲጽፍም የቻለውን ያህል የሟቹንና የገዳዩን ስም እያጣመረ ገልጾታል ፡

፩ኛ. አዝማች ሮቤል (ትግሬ) አራድ የሚባለው የግራኝ ጋሻ ጃግሬ የገደለውን የዓረብ ፋቂህ መጽ[illegible] አዝማች ሮቤል ያለውን የኛ የግዕዙ መጽሐፍ ጸሐፊ ላም ሮቤል ብሎታል ፤ አልቫሬጽ ደግሞ ባልጋዳ ሮቤል ትግሬ መኰንንነት የተሾመው ብሎት እንደነበረ ከዚህ በፊት አንብበናል (1) ። የዚህም ምክንያት እነአልቫሬጽ በነበሩበት ጊዜ (፲፭፻፲፪ - ፲፰) ባልጋዳ ሮቤል እየተባለ ትግሬን ይገዛ የነበረው በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ደግሞ (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) ጸሐፊ ላም ሮቤል እየተባለ አሁን በወሎ ጠቅላይ ግዛት ቀድሞ በቤተ አምሐራ ውስጥ የነበረውን አምባ ነገሥት የሚባለውን የነገሥታት ልጆች በግዞት የሚቀመጡበትን የግሼንን አምባ ይገዛ ነበር ማለት ነው ። እነሆ በዚህ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ሲዋጋ አራድ የሚባለው የግራኝ ጋሻ ጃግሬ ገደለው ።

፪ኛ፡ ዓረብ ፋቂህ ትንሽ አጻጻፍ ለውጦ ኤግባ ሚካኤል የሚለው ትክክለኛ ስሙ ዕቁበ ሚካኤል ሳይሆን አይቀርም ። ዕቁበ የሚለው ግዕዝኛ ቃል እንኳን ለባዕድ ለዓረብ ግዕዝ ለማያውቅ ለኢትዮጵያ ጸሐፊም ያዳግታል ። እርሱም የዚሁ የጸሐፊ ላም ሮቤል ታናሽ ወንድም ነው ። የዓረቡ ጸሐፊ ይግም (ግራኝ) ራሱ በጦር ወርውሮ ልቡን ወግቶት የጦሩ ጫፍ በጀርባው ወጣ ይልና የዕቁበ ሚካኤልን አስፈሪነቱንና ጀግንነቱን ጨምሮ ይገልጻል ። በዚህ መካከል የምንረዳው የሮቤል ቤተ ሰብ የጀግና ቤተ ሰብ ኖሯል ። ልጁ ዓምደ ሚካኤል ያባቱን ሹመትና ማዕርግ ከያዘ በኋላ ወደፊት በዝናው ዱር

(1) አልቫሬጽ . . . ምዕራፍ 45. 118

(ጅባት ?) ጦርነት በእንዴት ያለ ዝግንነት ተዋግቶ እንደሚሞት በሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ።

፫ኛ. ዓረብ ፋቂህ አዝማች መሕጠንቴ የሚለውን አዳም የሚባለው የሱማሌ ቀስተኛ ዓይኑን በቀስት መትቶ እንደገደለው ይናገራል ። የኛ የግዕዙ መጽሐፍ ይህን ሽም ጎዱግ ራስ ማኅፀንቶ እንዳለው ተመልክተናል ። ረኔ ባሴት ደግሞ አምሐ ጥንት ብሎት ይገኛል ፤ መቼም የኛ የራሳችን ታሪክ ነገሥት አንዱን ሰው ስሙን እየለያየ ስለሚጠራው ረኔ ባሴት ያንዱን መሠረት በማድረግ ይኸን ስም ተከትሏል ማለት ነው ።

፬ኛ. ባሕር ነጋሽ ዘወንጌል የደሆኖ ገኸ በአብድራዛቅ ቤን ሱሐሕ እጅ የሞተ ።

፭ኛ. ዣን በለው ራስ በኡስማን እጅ የሞተው ።

፮ኛ. ራስ ዓምዱ (ዓረብ ፋቂህ አዝማች አምዱ የሚለው) በአዳሙ እጅ የተገደለ ።

፯ኛ. ጃውሂርና መንዲል የሚባሉ ስልቦች የንጉሡ ግምጃ ቤቶች የነበሩት የንጉሡን ባንዲራ እንዲያዙ ቆመው ሳለ ጃውሂርን ኤሚር መሐመድ መንዲልን ድል ሰገድ የሚባለው ፈረሰኛ ገደላቸው ካለ በኋላ ዓረብ ፋቂህ ሕዝብ ሁሉ ቱንም የንጉሡ መሰል አድርጎ ይመለከታቸዋል ስለሚል የሊቃነ መኳስንት ደረጃ ያላቸውና የንጉሡ አሳሳች ያስመስላቸዋል ።

፰ኛ. ገብረ መድኅን (የሸዋው) ባንድ አኡማዳህ በሚባል ጥርሰ ቢስ ተመትቶ የሞተ ።

ISIC

፱ኛ. አዝማች ዘማንጃን (ዘመንክር ?) የራስ ወሰን ሰገድ ዘመድ በወዚር አዶሌ እጅ ተመትቶ የሞተ ።

፲ኛ. አዝማች ዋጅሙህ (ወገሙህ ?) በተከላይ እጅ የሞተ ። ሌሎቹን ሹማምንት መጠሪያ ስማቸውን ማግኘት ያልቻለውን በሹመት አገራቸው እንደዚህ ሲል ያወሳቸዋል ፡

(ሀ) የሸሬ ሹም በገራድ ዲን እጅ የሞተ ።

(ለ) የጸለምት ሹም አንድ እስላም የገደለው ይልና የቀሩትን ገዳያቸውን ያልታወቀውን

(ሀ) የአጋሜ ሹም ፡

(ለ) የተምቤን ሹም ፡

(ሐ) የጀጀራህ (ወገራ ?) ሹም ፤

(መ). የአበርጋሌ ሹም እያለ እነዚህ ሁሉ ሹማምንት በዚህ ቀን ውጊያ መሞታቸውን ያገልጽልናል ። ዮናኤል የሚባለው በናቱ በኩል ከንጉሡ የሚዛመድ ገራድ ሻሙን በሰይፍ እጁን ከቆረጠውና አብድ ኢን ናስር በጦር ከኋላው ከወጋው በኋላ አመለጠ ሲል በዚህ ጦርነት ከሞቱት ዝርዝር ለጥቆ ባለፈው የጻፈውን አንብበናል ። የሞቱትን ጠቅላላ የወታደር ቍጥር የኛን ፲ሺ ሲያደርግ የግራኝን ወገን በ፭ሺ ላይ ብቻ መድቦታል ። በሽሽት ጊዜ የሞቱት ሱማሌዎች ምናልባት እዚህ ቍጥር ላይ ራሱ አልደረባቸው እንደሆነ ፰ሺ ይደርሳሉ ማለት ነው ። ከነርሱ ወገን የሞቱትም ሹማምንት ቍጥራቸው በጣም ያነሰ ነው ። አውቆ ያሳንሰው ወይም

እስላሞቹ የአመካከትና ያመታት ዘዴ ቀደም አድርገው ከቱርክ፣ ወይም ከዓረብ አሠልጣኝ በመማር ተመትተው ከሚሞቱት እነሱ መትተው የሚገድሉት ይብዛ አናውቅም ።

ከነርሱ ወገን ይኸው ዓረብ ፋቂህ ካዘጋጀው የታሪክ መጽሐፍ በቀር ታላላቅ የትግሬና የአማራ ፡ የሸዋ ፡ የጸለምት ፡ የቤገምድር መኳንንትና ሹማምንት ከነወታደሩ የተላለቀበት ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው አዝማች የሆኑበት የዚሀ የሽምብራ ኩሬ ታላቅ የጦርነት ታሪክ በኛ በኩል በግዕዝ እንደ ዓረብ ፋቂህ ሰፋ አድርጎ ጽፎ ወደ ጊዜያችን ያስተላለፈው ስለሌለ የግራኝን የሹማምንቱን ዝግጅታቸውን የተዋጊውን መንፈስ ለውጊያ ለመቀስቀስ የተናገሩትን ዲስኩር ጸንተው መዋጋታቸውን በተመለከትንበት ዓይን የራሳችንም ወገኖች በምን አኳኋን እንደተዋጉና በመሸነፍ የደረሱበትን ምክንያት ጭምር ተመልክተን ሐተታ ለመስጠት አልቻልንም ።

የሆነ ሆኖ ዝርዝር ታሪኩን በኛ በኩል ብናጣውም የውጊያው መልክ በዚሁ የጠላት ወገን በሆነው በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ በሚታየው ብቻ የኛዎቹም በዚያው በግራኝ ሹማምንትና ወታደር አያያዝና ብርታት ጸንተው መዋጋታቸው የታወቀ ነው ። ነገር ግን ሰሎሞን ለሁሉ ጊዜ አለው እንዳለው የአክሱሙንና የላስታውን ዘመን ወደ ጐን እንተወውና ከይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት (፲፪፻፷፪ ዓ.ም.) እስከዚህ ዘመን (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) ድረስ የክርስቲያኖቹ ነገሥታትና የጦር መኰንኖቻቸው ሁል ጊዜ አሸናፊና አባራሪ ዘወትር ማራኪና አስገባሪ የነበሩት ባሁኑ ጊዜ እንደ ግራኝ አህመድ ያለ ሠራጦራ መሪ ጨካኝ ተዋጊ በአነጋገሩ ወታደር ቀስቃሽ ተነሥቶ በንጉሠ ነገሥቱ የተመራውን ብዙ ኃያላን የጦር አለቆች ያሉበትን ጦር አሸንፎ አገሪቱን ወረረ ። በፊቱ ያገኘውን ገዳምና ቤተ ክርስቲያን እያቃጠለ ሕዝቡንም እያሰለመ ያለፈውን ሁሉ ደም በእጥፍ ተበቀለ ።

በዚህም ላይ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የዓፄ ልብነ ድንግልንና የፖርቱጋልን ነገሥታት የወዳጅነት ግንኙነት በክፉ ዓይን የሚመለከቱ የቱርክና የዓረብ አገር ባለሥልጣኖች በነርሱ ደጋፊነት ከየአለበት የመጡት በውጊያ የሠለጠኑት የቱርክ ፡ የዓረብ ፡ የፋርስ ፡ የሕንድ አዳዲስ የዘመኑን መሣሪያ ይዘው የመጡት ጥርቅም ወታደሮች የንጉሡን ጦር እንዳጠቁና የግራኝ አህመድን ድል እንዳረጋገጡለት መገንዘብ አለብን ። በውጊያው ላይ ያልተላየው ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ በጽሑፉ ውስጥ የባሕር ወታደሮች የፈረሶቻቸው ቅልጥም እስኪታጠፍ ወፍራም አቧራ ቆሞ እስኪሄድ ድረስ በኃይል ተዋጉ ያላቸው እነሱን ነው ። እነሱም የያዙት መሣሪያ ምንም እንኳ ዓረብ ፋቂህ እዚህ ላይ ባይጠቅሰው ዘመናዊ ነፍጥና መድፍ ጭምር መሆን አለበት ።

በአልቫሬዝ መጽሐፍና ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ነገሥታት ለአማኑኤልና ለዮሐንስ ፫ኛ በጻፉቸው ደብዳቤዎች ውስጥ እንደተገነዘብነው ዓፄ ልብነ ድንግል ኃይላቸውን ከፖርቱጋል ኃይል አስተባብረው የእስላሞቹን ኃይል ከኢትዮጵያ ወደብ ለማባረር ብቻ ሳይሆን የመሐመድ መቃብር ያለበትን

መስጊድና የሚካን ከተማ ለማፍረስ ኢየሩሳሌምንም ለማስለቀቅ የነበራቸው ትን ቢትና ምኞት ከመፈጸሙ በፊት ይኸን መንግሥት ማጥቃትና ማስጠቃት ለቱርኩ ቹም ሆነ ለዓረቦቹ ግዴታቸው መሆኑን በእውነተኛው ፍርድ መመልከት አለብን። ዓረብ ፋቂህ ባይጠቅሰውም ጦርነቱ የተዠመረው ፖርቱጋሎቹ የዚህን ዓላማ የያ ዘውን ያዒ ልብነ ድንግልን ደብዳቤ ይዘው ወዳገራቸው እንደተመለሱ ነው ።

ከቀድሞ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ዠምሮ የወላስሞቹ ሱልጣኖች የዓረቦቹን እር ዳታ እየያዙ በአዳል በኩል እንደተዋጉ አሁንም ግራኝ የተነሣው በዚሁ እርዳታ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት በሩቅ ካለው ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር በበኩሉ ለመወዳጀት ያደረገው እርምጃ አግባብ ያለው መሆኑና ከዚህ ሌላ የተሻለም ማግረጫ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዳልነበረው የታወቀ ነው ።

ዳሩ ግን ለጊዜው ግራኝ የተጠቀመበት ዓፄ ልብነ ድንግል የተጐዱበት ዋነ ኛው ምክንያት ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የዓፄ ልብነ ድንግል ረዳት ፖርቱ ጋል ከ፰ሺ ኪሎ ሜትር የበለጠ ርቆ ለጊዜው ምንም ማድረግ ሳይቻለው ለግራኝ እርዳታ የሚያቀብሉት የጅዳ የአደን የዘቢድ ታሻዎች ግን ካጠገቡ ስለሆኑ ነው ፤ ተረጂውንና ረዳቶቹን ከቀይ ባሕር በቀር የሚለያቸው የለም ። የሚቃወም የኢት ዮጵያ ነዋሪ ወታደር በየወደቡ ስለሌለ በቅርቡ በምጥዋ በዙላ በተለይ በዘይላ እነ ዚህ ወደነዚያ እነዚያ ወደነዚህ እንደልብ በመርከብ እየተመላለሱ ወታደርና የጦር መሣሪያ እያመላለሱ የአጥቂነት ዓላማቸውን ፈጸሙ ። ዓፄ ልብነ ድንግል እኔ ስንቁን ልቻልና የእናንተ ወታደር በየወደቡ መጥቶ ይቀመጥ ብለው ለፖርቱ ጋል ንጉሥ ከአራት ዓመት በፊት በደብዳቤ አሳስበውት የነበረው ይህ እንዳይደ ርስ ነበር ። ነገር ግን ይህ ዓላማ በርቀት ምክንያት ወደ ፍጻሜ ሳይደርስ ግራኝ በቅ ርብ በሚያገኘው እርዳታ ተደግፎ ያለረዳት በጠላት የተከበበውን ያዒ ልብነ ድንግ ልን መንግሥት እንደልቡ በውጊያ ያዋክብ ዠመር ።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ባገሪቱ ላይ የተነሣው ጦር ቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታትና የወላስማ ወገኖች ከሚያደርጉት ውጊያ የተለየ በደ ንብ በየላን በታላቅ ድርጅት የተዘጋጀ ነው ለማለት ይቻላል ። ግራኝ አህመድ ራሱ በጠባዩና በፍጥረቱ ካለው የመሪነቱ ችሎታ ከጉብዝናውና ከድፍረቱ በቀር ይኸን ከበላይ ታላቁ የቱርክ መንግሥት የሚደግፈውን ጦርነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ታላ ላቅ የታወቁ የዓረብ ሼኮች እንደ አቡበክር አርሾናህ ያሉት በየጦርነቱ ዋዜማ ሲነ ገር ሲደገም የሰማነውን በየገጹ ግርጌ የጠቀስነውን ከቁራን ልዩ ልዩ ምዕራፍ (ሱራት) እየጠቀሱ ርቱዕ በሆነው አንደበታቸው ከውጭ የመጡትንም ቱርኮችና ዓረቦች ከውስጥ ያሉትንም የአዳልና የሱማሌ እስላሞች «ጀሃድ-ቅዱስ ጦርነት» አሰኝተው በማወጅ በመልፈፍ በማስለፈፍ የተዋጊውን መንፈስ በደንብ አዘጋጅተ ውት ስለነበረ በዚህ ዓይነት የተዘጋጀው ቁራጥ ወታደር በክርስቲያኖቹ በኩል ያል ታሰበውን ድል አገኘ ።

ከዚህ ሁሉ አልፈን በዚህ ጦርነት ደግሞ በተጨማሪ የምንመለከተው መንግ

ሥት ሰማያትን ከሚያስገኘው ከቅዱሱ ጦርነት በቀር የኢትዮጵያንና የፖርቱጋልን የግንኙነት ውጥን ለማጥፋት የቱርክ መንግሥት ከወሰደው እርምጃ በላይ ራሱ ስመ ጥር የሆነው «እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ኮከብ» የበረከተው የኢትዮጵያ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት የደለበ ሀብት የቱርኩንና የዓረቡን የፋርሱን እስላማዊ ተዋጊ ሁሉ ለዘረፋ አስጐምጅቶታል ። ከፊተኛው ከደቀርውና ከሁፋቱ ጦርነት የተገኘውን የምርኮ ሀብት ግራኝ ሆን ብሎ ለዓረብ አገር ባላባቶች እየመረጠ ልኮ እንደነበረው ሁሉ የዚሁ ወሬ በያለበት በጀላ በእደን በሐድራሞት በመስቃን ስለተሰማ በወርቅ ከደለበው ሀብታም አገር ምርኮ ለማግኘት የመጣው ሁሉ የግራኝን ጦርና ትጥቅ በደንብ አደርጅቶለታል ። ስለዚህ እያንዳንዱን እስላማዊ ተዋጊ የሃይማኖት ፤ የጥቅም ፤ የፖለቲካ ጉዳይ ተያይዞ ይገፋፋዋል ማለት ነው ፡

እነዚህም አብዛኞቹ የቱርክ ፣ የዓረብ ፣ የፋርስ ፣ የሕንድ ተወላጆች ዘራቸው ቢለያይም በሃይማኖት አንድነት የተሣሠሩ የቱርክ ሡልጣን ሰሊም ፩ኛና ልጁ ሶለይማን የባልካንን አገሮች እንደዚሁም የሦርያን ፣ የግብፅን ፣ የፓለስቲንን አገር ሲወርሩ አብረው የተካፈሉ ሰፋ ያለ የጦር ልምድ ያላቸው ይኖሩባቸዋል ። በእጃቸውም ያለው የጦር መሣሪያ ቶጥሀን ከሲም ፓሻ በሚባለው የጥይትና የመድፍ ፣ የባሩድ ፋብሪካ ቤቶች ያፈራቸውን ስለሆነ እነዚህን አዳዲስ መሣሪያዎች የያዙ የሠለጠኑ ተዋጊዎች በግራኝ ጐን መሰለፋቸው ጦርነቱን መካፈል ለግራኝ አህመድ ድልዋና አብነት ሆኖታል ። እነዚህ ባይደረቡ ኖሮ ግራኝ ምንም ራሱ ጀግና ቢሆን ባገር ተወላጅና ቍጥሩ ባነሰ ጦርና የጦር መሣሪያ በበኩሉ ዝግጁነቱ የታወቀውንና ይኸን ያህል ቍጥሩ የበዛውንና የደረጀውን የንጉሠ ነገሥት ጦር ምናልባት ለማሸነፍ ባልቻለም ነበር ። ዓረብ ፋቂህ የባሕር ወታደር በሚል ስያሜ ጦርነቱን መካፈላቸውን ባለፈው እንዳነበብነው ሲጠቅስ የመሣሪያውን ዓይነትና ብዛት አስተካክሎ ባይጽፈውም ሰዎቹ ካሉ ባዶ እጃቸውን እንደማይመጡ የታወቀ ነው ። በክርስቲያኖቹ እጅ የሌለ አዳዲስ መሣሪያ ባይዙ ኖሮ ከነርሱ አምስት ጊዜ እጥፍ የሆነውን ጦር እንደምን ያሸንፉ ነበር ያሰኛል ።

ISJC

ዓረብ ፋቂህ ለዚህ ለሽምብራ ኩሬ ጦርነት ግራኝ አህመድ አስከትሎት የነበረው የፈረሰኛ ወታደር ቍጥር ፭፻፰ የእግረኛውን ፲፪ሺ አድርጎታል ። ከጦርነቱ በኋላ ተማርኮ በአጠገቡ የነበረው አዝማች ሐይቢ እንዳስረዳው የንጉሡ ጦር ፲፮ሺ ፈረሰኛ ከ፪፻ሺ በላይ ሰይፍ ፣ ጦር ፣ ቀስት የያዙ የእግረኛ ወታደሮች እንደነበሩ ይገልጻል ። ስለዚህ እንደዚህ ባነሰ ጦር ቍጥሩ ይኸን ያህል የበረከተውን የንጉሡን ጦር ለማሸነፍ የቻለው የነዚያ የስልጡኖቹ ወታደሮች ከነመሣሪያቸው ተካፋይነት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ቍጥሩ ያነሰ የሠለጠነ ያንድ አገር ጦር ብዙውን ያልሠለጠነውን የሌላውን አገር ጦር በጦር ሜዳ ሲያሸንፍ በታሪክ የመዠመሪያ ጊዜ አይደለም ። ለምሳሌ በቅርቡ ጊዜ ፱፻ የማይሞሉ የፈረንጅ የግዥ ወታደሮች (መርሰኔር) በኮንጎ ግዛት በቡካቡ ገብተው ሳለ ፴ሺ የሚሆነው የኮንጎ መንግሥት ወታደር በኀይል ማስወጣት አቅቶት በግልግል ብቻ ለቀው ወጥተዋል ። ቍጥራቸው ፫ ሚሊዮን የማይሞላው

እሥራኤሎች የሕዝቡ ጠቅላላ ቍጥር ከ፵ ሚሊዮን ከሚበልጠው ከግብፅ፣ ከሶርያ፣ ከዮርዳኖ ወታደሮች ጋር ተጋጥመው አሸንፈዋል ። በጥንት ታሪክ ደግሞ ታላቁ እስክንድር በ፫፻፴፩ ዓመት ክልደት በፊት ፵ሺ የሠለጠነ የግሪክን ወታደር ይዞ ፩ ሚሊዮን ጦር የያዘውን የፋርሱን ንጉሥ ዳርዮስን በአርቤል አሸንፎታልና የዚህ ዓይነቱን ምሳሌ ብንዘረዝረው ማለቂያ የለውም ።

አንዳንድ ጊዜ ሁለቱም ባለጋራዎች ሥልጣኔያቸውና የያዙት መሣሪያ የሚመዛዘን ሆኖ ሳለ በአመራር አቅድና የጦር ስልት ወይም በምቹ ሥፍራ አመራረጥ «ስትራተጂክና ቴክኒክ» ምክንያት አንዱ ወገን የተዋጊው ወታደር ብዙም ቢሆን ከመሸነፍ አይድንም ። አንዱ ንጉሠ ነገሥት ናፖሌዎን ሁለቱን የነምሳንና የጀርመንን ነገሥተ ነገሥታት በ፲፰፻፭ ዓ. ም. አውስተርሊዝ ላይ ያሸነፋቸው በጦር ስልቱና በዘዴው ነው ። ያለዚያ የሁለቱም ወገን ጀርመናዊና ፈረንሳዊ ሕዝብ ሥልጣኔያቸውም መሣሪያቸውም ጉብዝናቸውም ተመሳሳይ ነው ።

እንደዚሁም በሽምብራ ኩሬ ጦርነት የክርስቲያኖቹን ጉራ የጠራ የዘመኑን መሣሪያ የያዙ የሠለጠኑ ተዋጊዎች የጦር ስልት ስለጐደለው ተሸንፎ የማያውቀው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በ፲፱ሺ. ቍጥሩ ፪፻ሺ የእግረኛ ፲፯ሺ የፈረሰኛ ጦር የሚሆነው የእግረኛ በ፰፻፳ የፈረሰኛ ጦር ተሸንፎ ከመሸሸ ደረሰ ። ጉዳዩ ለወደፊት ታላቅ ጦርጦራ ትምህርትና ጥንቃቄ የሚወሰድበት ነው ። ወደ ፊት እንደ ግራኝ ያለ የሽምብራኩሬን ጦርነት የመሰለ በጊዜ መሪ የተማረም ጦር ይዞ በመነሣት ሌላ ያችን ያለ ጊዜያችንም ሊገጥም ይችላል ። መመለሻው ግን የሁሉም ቀደም ብሎ በሚደረግ ጥናትና ዝግጅት መሆኑ የታወቀ ነው ። በምድራውያን መንግሥታት መካከል የሚደረግ ጦርነት ሁል ጊዜ ሊታገድ የሚችለው ከራስ በሚገኝ ኃይል ብቻ ነው ። ይኸውም ማለት መሣሪያው በመሣሪያ እቅዱ በእቅድ ነው እንጂ ከዚህ ውጭ የለም ። የዓለም ማኅበር ወይም የወዳጅ እርዳታ የሚባለው ሁሉ መሠረት በሆነው በራስ ኃይል እንደተጨማሪ መሆኑን ያለፈው ታሪክ በሰፊው አመልክቷል ። ጠላትን መናቅ ደግሞ ከሁሉ የበለጠ ከፍ ያለ ስሕተት መሆኑን ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት በቀላሉ ለመማር ይቻላል ።

## ምዕራፍ ፵፩

## በደዋሮ የግራኝና የራስ ነቢያት ጦርነት (፲፰፻፳፱ ዓ. ም.)

እስካሁን የተደረጉት ጦርነቶች የተከናወኑት በኢትዮጵያ ምሥራቅ በታላላቆቹ አውራጃዎች በይፋትና በደዋሮ በፈጠጋር የሆኑበት ምክንያት በዝዎግራፊው ካርታ ላይ እንደሚታየው እነዚህ አውራጃዎች ለአዳል አገር ወሰነተኛ ግራኝ ከዓረቦቹ አገር ከጅዳና ከዘቢድ መሣሪያና የቅጥር ወታደር ሊያገኝበት የሚችለውና በርሱ ሙሉ ቍጥጥር ውስጥ የሚገኘው የዘይላ ወደብ በነዚሁ በደዋሮና በይፋት ትዩዩና ቅርብ በመሆናቸው ነው ።

ከዚህም ጋር በይፋትና በደዋሮ የሚገኙት ትክለኛ ባላባቶች ከኡመር ወላስማና ከሐይደራ ዝምሮ እስላሞች ከንዋሪው ሕዝብ ውስጥም ከክርስቲያኑ እስላሙ መብለጡን ትክክለኛ የሂሳብ ግምት ባይኖረንም በብዛት የእስላምን ሃይማኖት ያቀፈ ስለሚገኝ እነርሱም ልባቸው ወደነዚያ እየደላ ይህ ሁሉ ተደራርቦ መንገድ በመምራትም ማስረጃ በማቀበልም ረገድ ግራኝ አህመድ እንደልቡ በነዚህ የሃይማኖት ወገኖቹ ሊጠቀም ችሏል (1)። በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. ዓፄ ልብነ ድንግል ከግኅቶዝ ጋር የተዋጉና ማኅፉዝ በጦርነቱ ላይ በአባ ገብረ እንድርያስ እጅ ሲሞት የበላይ አዝማቹ መሐመድ ኢብን አዝሐር ከጦርነቱ ቦታ ከሸሸ በኋላ ዘለቁታውን እምልጦ ወደ አዳል አገር ሒሬና ሊደርስ የቻለው የደዋሮ ሰዎች በቤታቸው ደብቀው መንገድ መርተው ስለረዱት ነው (2)።

ወደፊት በክርስቲያኖቹ አውራጃዎች በሸዋ ፣ በጐጃም ፣ በቤተ አምሐራ፣ በበጌምድርና በትግሬ በየጦሩ ግንባር የግራኝ ማሸነፍ እየቀጠለ መሄዱ ባይቀርም የመገርመሪያዎቹን ድሎች በራስ ደገልሃንና በነወናግ ዣን ላይ በይፋትና በደዋሮ በቅድሚያ ያገኘበት አንደኛው ምክንያት እላይ እንዳመለከትነው የነዋሪውን ሕዝብ እርዳታ ማግኘቱና ከጀርባውም በቀጥታ በሃይማኖት ወገኖቹ (ዓረቦች) እርዳታ በመደገፉ ነው ።

በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. አካም ላይ አዛዥ ደገልሃን ከተሸነፈ ወዲህ የራስ ደገልሃንን ሁኔታ ዓረብ ፋቂህ በመ[illegible]ፉ አይገልጽም ። የዓረቡ ጸሐፊ በወገኑ በግራኝ ግንባር ያለውን ሁኔታ በዝርዝር እንደሚጽፍ በክርስቲያኖቹ በኩል ያለውን ራሱ በአካል የሌለበትን በዚያው መጠን ለመዘርዘር ያዳግተዋል ። ምናልባት ይህ የጦር መሪ ከአካም እምልጦ ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ከሄደ በኋላ ተግሣጽ አግኝቶት በርሱ ፈንታ በደዋሮ ራስ ነቢያት ተሾሞ ይሆናል ። የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ መሾሙን ሳያመለክት በዚህ ጊዜ (በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. መጨረሻና በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ) በደዋሮ ከፋኑኤልና ከደገልሃን ወዲህ የግራኝን የወረራ ጦርነት አጥብቆ የተቃወመ ይህ ራስ ነቢያት መሆኑን ያመለክታል ። ይኸን ታላቅ መኰንን ዓረብ ፋቂህ ራስ ባንያት ይለዋል ። ነገር ግን የኛ የግዕዙ ጽሑፍና በቅርብ የተዋወቀው አልቫሬዝ ነቢያት ስለሚሉት ትክክለኛ ስሙ ነቢያት መሆን አለበት ።

አልቫሬጽ ስለራስ ነቢያት ቀጥሎ ያለውን ይጽፋል «. . . . . በዚያ አገር (በኢትዮጵያ) በቆየንበት የስድስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አራት ባሕር ነጋሾች ተለዋውጠዋል ፤ ከነዚህም ውስጥ እኛ በደረስን ጊዜ የነበረው ባሕር ነጋሽ ዶሪ ነበር ። እርሱ ሲሞት በንጉሡ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ቡላ ለተባለው ዕድሜው ፲ ወይም ፲፪ ዓመት ለሆነ ለሚስቱ ልጅ ተላለፈ. . . . . . ። በኋላ ወጣቱ ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ተጠርቶ ይህ ማዕርግ ተወሰደበትና ራስ ነቢያት ለተባለ ለአንድ መስፍን ተሰጠ ። ራስ

(1) ያምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ገጽ ፤ ፔሩሾ ያሳተመው 294 ፤
(2) ዓረብ ፋቂህ የረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 61 የማስታወሻ ቍጥር 1 ።

ነቢያት በዚህ ማዕርግ (ባሕር ነጋሽነት) ሁለት ዓመት ካገለገለ በኋላ እርሱ ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርቶ የቢትወደድነት ማዕርግ ሲሰጠው ባሕር ነጋሽነቱ አዲቢ ለተባለው ተሰጠ» ይልና ቀጥሎ በሌላ ቦታ ላይ ዋናው መላክተኛ ሮድሪግ ደ ሊማና ምክትሉ ዦርዥ ደ አብሬው ተጣልተው ስለነበረ እነርሱን ለማስታረቅ ፖርቱጋሎቹ ወደ አገራቸው ለመመለስ ወደ ምጥዋ በሚጓዙበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ ለነርሱ የተላከውን ስጦታ ለማድረስ ከተመደቡት ሁለት ታላላቅ መኳንንት አንደኛው ራስ ነቢያት እንደነበረ ያወሳል (1) ።

ይህ የአልቫሬዝ አጻጻፍ ትክክለኛ መሆኑ በኛው የግዕዝ ጽሑፍ የጸደቀ ነው ። ዓፄ ልብነ ድንግል ለደቅ ማርያም ከሠራዪ እንደዚሁም ለደባርዋ ሚካኤል ርስተ ጉልት አድርገው በሰጡበት ዘመን የሠራዬ ሹም አሮን ፣ የአክሱም ንቡረ እድ ኖብ፣ ቆሰ ገበዝ ኢያቄም በነበሩበት ዘመን ራስ ነቢያት ባሕር ነጋሢ ተብሎ አብሮ በገ በዘ አክሱም መዝገብ ላይ ስሙና ማዕርጉ ተጠቅሷል ። በሌላ ላይ ደግሞ ዓፄ ገብረ መስቀል የመደራን ምድር ለአባ ገሪማ መታሰቢያ ሰጥቶት የነበረውን ዓፄ ልብነ ድንግል ያለፈውን በማደስ የጣፋ ቆላ ምድር ሌላም ከየቦታው በጕለቱበት ጊዜ የነ በሩትን የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች በጠቀሱበት ጽሑፍ ላይ ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስና ከዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ቀጥሎ ቢትወደድ ራስ (ሮስ ?) ነቢያት ተብሎ ተጠቅሶ ከርሱ ተከታትለው ግራ ጌታ ዘድንግልና ንቡረ እድ ፍትሐሙ ቆሰ ገበዝ ኢያቄም . . . . . ተጠቅሰዋል (2) ።

ስለዚህ ራስ ነቢያት በዚህ ዘመን ካሉት ታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት እን ደነ ራስ ወሰን ሰገድ ፤ እንደነራስ ማኅፀንቶ ፤ እንደነ ቢትወደድ ሠርፄ ፤ እንደነ ራስ እስላም ሰገድ የሚቆጠር ነው ማለት ነው ። በዚህ ዘመን ካሉት ባለሥልጣኖች ጳጳ ሱን ወደ ጐን አድርገን ከንጉሠ ነገሥቱ በሥልጣን የሚከተለው ዓቃቤ ሰዓቱ ሲሆን ከርሱ የሚቀጥለው ቢትወደዱ ነው ። ነገር ግን ቢትወደዶች የግራና የቀኝ ተብለው ባንድ ጊዜ ስለሚሾሙ ራስ ነቢያት የቀኝ ቢትወደድ በተባለበት ጊዜ የግ ራው ደግሞ ቢትወደድ ሠርፄ ነበር (3) ። ነገር ግን ከቀኙ የግራው ብልጫ ስለ አለው ከነቢያት ሠርፄ ቅድሚያ አለው ማለት ነው ። ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ ይኸው ራስ ነቢያት ደዋሮን ሊከላከል መጥቷል ማለት ነው ።

በዚህ ምክንያት ዓረብ ፋቂሀም በበኩሉ ይኸንኑ ታላቅ መኰንን በቤተ መን ግሥቱ ዘንድ ያለውን ከፍተኛ ሥልጣን በማውሳት ጠባዩንና ተከላካይነቱን ከማ

(1) አልቫሬዝ . . . . ምዕ. 24 ምዕ. 108

(2) ወካዕበ እምነ ሠራዌ ጉለትኩ (እነ ልብነ ድንግል) ጉልት ቤት ገበዝ ለማርያም ዘደቅ ኢታ . . . . ወካዕበ ጉለትኩ ለሚካኤል ዘደባርዋ ጉልተ . . . . . እንዘ ባሕር ነጋሢ ራስ ነቢያት ወእንዘ ንቡረ እድ ኖብ ። በእኩቴተ አብ . . . . . ዘወሀበ ንጉሥነ ገብረ መስቀል ለመከነ መደራ (መጠራ ?) ለተዝካረ አቡነ ገሪማ ሐደስኩ አነ ልብነ ድንግል ወስመ መንግሥትየ ዳዊት ምድረ ጣፋ ቈላሃ ወደጕዓሃ ወዓድዋ . . . . እንዘ ጳጳስ አባ ማርቆስ ወዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ወብሕትወደድ (ሮስ) ራስ ነቢያት . . . . መጽሐፈ አክሱም ኮ. ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 26 ፣ 31 - 32 ፣ 33 ።

(3) መጽሐፈ አክሱም ኮ. ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 33

ጥላላት ጋር እንደዚሁ ሲል ያመለክታል «በደዋሮ ራስ ባንያት (ነቢያት) የሚባል ታላቅ ሹም ነበር ። እርሱም በንጉሡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት ስለነበረው በሌሎቹ ላይ የበላይነት ሥልጣን ሰጥቶት ነበር ፤ ጥብቅ ኩሩ የሸፈተ ሰይጣን ነበር ። እስላሞቹ አገሩን ወርረው መዝረፋቸውን ከሰላዮቹ በሰማ ጊዜ ወታደሩን ሰብስቦ መተላለፊያ የሌለበትን ጠባብ መንገድ ይዞ ይጠባበቅ ገ መር» (1) ። ኩሩ ሰይጣን የሚል ቅጽል የዓረቡ ጸሐፊ ለነቢያት የሰጠበት ምክንያት ደህና አድርጎ በመከላከሉ ላይ ሆን አይቀርም ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ ታላቁን የሽምብራ ኩሬን ጦርነት በአለፈው ዓመት ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. መጋቢት ፲፮ ቀን አግኝቶ ወዳገሩ ተመልሶ የሻዕባንና የረመዳንን የሸዋልን የጾም ጊዜ በሐረር ከአሳለፈ በኋላ (2) በዋቢ ሸበሌ አድርጎ ደዋሮ ሲደርስ ጦሩን ከሁለት ከፍሎ አንዱን ክፍል ለራሱ አስቀርቶ ሁለተኛውን ለወዚር ኑር ቢን ኢብራሂም ሰጥቶ ወደ ደዋሮ ጉዞ ገ መሩ ።

በዚህ ዓይነት ሲጓዙ ኩሽም አቡበከር የሚባለው ከአራት የፈረሰኛ ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ፈረሰኞቹ ከዋናው ጦር ተለይተው ቀድመው በሸለቆ ውስጥ በሚጓዙበት ጊዜ ከአንድ ቍጥሩ በርከት ካለ የክርስቲያን ጦር ጋር ተገናኝተው ክርስቲያኖች በኃይል ስለወጉዋቸው እስላሞቹ ወደ ኋላቸው ሸሹ ። ኩሽም አቡበከር የሚባለው ግን «ቅዱስ ጦርነት በአላህ መንገድ» እያለ በመጮህ ሲዋጋ ከዚያው ከጦርነቱ ላይ ሞተ ።

ISIC

ዋናው በግራኝ አህመድ የሚመራው ጦር በደዋሮ ውስጥ ገብቶ በተለይ አዳል መብረቅ ከሚባለው ወረዳ ሲደርስ የዚሁ ወረዳ ገዥ አቤል የሚባለው እስከሚቻለው ከተከላከለ በኋላ በመጨረሻ ወታደሩ ሲሸሽ እርሱ ተማረከ ።

ግራኝ አህመድ አቤልን እንዳሠረ ወደፊት ሲጓዝ ራስ ነቢያት ከነጦሩ ወደ ሠፈረበት ጠባብ ቦታ ተጠጋ ። በዚያን ጊዜ ምክር ተያዘና ግማሹ በጣም ከመንገድ ርቀን ወደ ውስጥ ስለገባን መውጫ የለንም ሲሉ የቀሩት እምነታችንን በእግዚአብሔር ጥለን እንዋጋ አሉ ። ከዚህ በኋላ ግራኝ አቤልን እንደታሠረ አስጠርቶት እፊቱ አቁሞ «ስማ ወደፊት ስንጓዝ ጠላቶቻችን መንገዳችንን የቆረጡብን እንደሆነ በመጀመሪያ አንተን ገድለን ቀጥሎ ከነርሱ ጋር ስንዋጋ ለቅዱስ ጦርነት ስንል ብንሞትም ደስ ይለናል» ቢለው አቤል «ይኸ ጥሩ አሳብ አይመስለኝም ይልቅስ በነርሱ ዘንድ ያሉትን የንጉሡን አብያተ ክርስቲያናት ላታቃጥሉ ቃል ትገቡልኝ እንደሆነ መንገዱን በሰላም እኔ ላስለቅቅላችሁ» አለ ። ግራኝም ይኸንኑ አሳብ ተቀብሎ «እስላሞቹ በዚያ ያሉትን አብያተ ክርስቲያን ላያቃጥሉ አንተም መንገዱን ልትለቅላቸው በዚህ ቃል ገብተዋልና መንገዱን ለቀህ አስተናግዳቸው ይኸን አሳብ እምቢ ብለህ ጦርነት ሆኖ ከተሸነፍህ በኋላ የንጉሡ አብያተ ክርስቲያናት የተቃጠሉ እንደሆነ ኃላፊው አንተ ነህ» ። ብሎ አቤል ለነቢያት ላከበት ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 135

(2) የነዚህ የአጽዋማት ወራት እንደ ጨረቃው አኳኋን በያመቱ ይለዋወጣሉ ። ባሴት ሬ ግን በሚያዝያ ፣ በግንቦት ፣ በሰኔ ላይ አድርገውታል (ገጽ 131 ማስታወሻ 3) ።

እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ራስ ነቢያት ይኸንኑ ውለታ በመቀበሉ ግራኝና ሠራዊቱ በዚያ በጠባቡ መንገድ እንደልባቸው አልፈው ወረቀሎ በሚባለው ወረዳ በተለይ ማሺብ ወደሚባለው ሥፍራ ደርሰው ብዙ ምርኮ እንዳገኙ ከዚያ አልፈው ጃን አምባ በሚባለው አውራጃ ገብተው ማይ - ፋላ ደርሰው በዚያም ብዙ ምርኮ እንዳገኙ ያረጋግጣል (1) ።

ከዚሁ አያይዞ በዚህ አገር ራጅህ የሚባል ከእስላሞች አገር መጥቶ ክርስትና ተቀብሎ ከንጉሡ መሬት ተሰጥቶት ይኖር ነበርና ግራኝ "እስላም የእስላም ልጅ ራስህ ተዋጊ የተዋጊ ልጅ የነበርህ ነህና ወደኛ ወደ ወንድሞችህ ተመለስ ባለፈ ነገር ተስፋ አትቁረጥ" የሚል መልእክት ስለላከበት ራጅህ እሺ ብሎ ወደ ግራኝ ተመልሶ እንደ ገባለትና እንደሸለመው ራጅህም አገሩን በሙሉ ወጣ ገባውን ያውቀው ስለነበረ ግራኝ በርሱ እየተመራ ከደዋሮው ከፋኑኤል ጋር ትንሽ እንደተዋጋ ፋኑኤልና ክርስቲያኖቹ እንደሸሹ በያለበትም እየተዘዋወሩ እንደልባቸው የተበታተነ ጦርና መንደር አግኝተው ብዙ ምርኮ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ።

ይህ ያሁኑ የግራኝ ጉዞ ደዋሮ በሚባለው በዚያን ዘመን ታላቅ አውራጃ በነበረው ውስጥ መሆኑን ያረቡ ጸሐፊ እያመለከተ የደረሱበትንና የተዋጉበትን ቀበሌ በዚያን ዘመን አጠራር አዳል መብረቅ ማሺብ ወረቀሎ ዣን አምባ ማይ ፋላ እያለ ያወሳል ። እነዚህ ቀበሌዎች ይኸን ስም እንደያዙ እስከ ዛሬ ስለአልቆዩና ከዚያ ወዲህ በጋልኛ ስያሜ ስለተለወጡ ሥፍራቸውን በአሁን ሰዓት በትክክል ለመለየት ወይም የዛሬውን አጠራር ከዚህ ከቀድሞው አጠራር ጋር አገናዝቦ ለማመልከት ይቸግራል ። ግራኝ ዓፄ ልብነ ድንግልን ባለፈው ዓመት ድል የመታበት ሥፍራ ያን ጊዜ ሽምብራ ኩሬ በተባለው ዱከምን ወንዝ ተሻግሮ በዛሬው ቢሾፍቱ ቀበሌ (ምናልባት በጨለቅለቃ ኩሬ) ስለሚመስል ሙሴ ባሴት ረኔ እንዳሉት ያሁኑ ደግሞ ጉዞውና ውጊያው ከዚያ ታች ታቹን ባሩሲና በከምባታ ሰሜናዊ ጫፍ አድርጎ ወደ አሞና ወደ ጊቤ ወንዝ አቅጣጫ ይመስላል ።

ISIC

ግራኝም ይኸን ሁሉ ሲያደርግ ግማሹን በዘዴ በስለላ ባገር መሪዎች በመጠቀም አልሆን ሲል ደግሞ ጨክኖ በመዋጋት ከድል ወደ ድል እየተራመደ እስከዚህ ደርሷል ። በአቤል እስረኝነት ራጅህ በሚባለው ቀድሞ እስላም በኋላ ክርስቲያን በነበረው ሰላይነትና መሪነት በደንብ ተጠቅሞባቸዋል ። ባለፈው በንጉሡ ላይ ያገኘው ድል የራሱንና የጦሩን ዝና በጣም ከፍ ያለና የማይበገር አድርጎ ስለአስገመተው እስካሁን ድረስ ወደ ንጉሡ የነበሩት የእስላም ነክነት ያላቸው ሁሉ በየጊዜው እየገቡለት የራሱን ኍራ አደርጅተውለታል ። መቼም በማናቸውም ዓለም እንደሚደርሰው በተሸናፊ ላይ ከዳተኛ ይበዛል ። ለአሸናፊ ደግሞ ታማኝ መስሎ አዲስ የሚገባለትና የሚያከነፍስለት አገልጋይ በዚያው መጠን ብዙ ነው ።

(1) ማይ ፋላ ማለት የውሀ ሸለቆ ማለት ነው ሲሉ ረኔ ባሴት የተረጐሙት ልክ አይመስልም ይልቅስ ፍል ውሀ ባይሆን አይቀርም ቀበሌውም የዛሬው መተሐራ ይሆን ይሆናል ።

ስለዚህ ግራኝ እስካሁን ያገኘውን የበረከተ ምርኮ በወዚር አቦሌ ጠባቂነት ከ ጓዙ ወደ ኋላ ትቶ እርሱ ወደ ፊት እየገፋ ራስ ነቢያት ወደ ሠፈረበት ቀበሌ ምር የሆኑትን የፈረሰኛ ወታደሮቹን እንደያዘ ገሠገሠ ። በዚህም ጊዜ ቀድሞ በነበሩት መሪዎች ላይ ዋና መሪና አስተናባሪው አውራጃውን ሁሉ የሚያውቀው ድል በበ የሚባለው በተጨማሪ ስለገበረለት የግራኝ የወረራ ጉዞው ሁልጊዜ ከመቃናት አ ለፈም ።

በዚህም ምክንያት ግራኝ ራስ ነቢያትን ፍለጋ ወደፊት በሚገፋበት ጊዜ የ ዋሮው ፋኑኤል እንደዚሁም ባንድ በኩል ከፋሌ በሌላ በኩል ቃውሊ ከዚያም ዘን (ዜና ?) የሚባሉ ሹማምንት እንደተዋጉትና ከፋሌም ቃውሊም ዘንም ሲማረኩ ፋ ኤል ብቻ በድፍረት ወደፊት መጥቶ ኢማር አህመድ ከሚባለው ጋር ተጋጥ አንድ ላንድ ከተደባደበ በኋላ አዝማሚያውን አይቶ እንደሸሸ ያረቡ ጸሐፊ ያመ ክታል (1) ።

ከዚህ ሁሉ ዝርዝር ጦርነት በኋላ ወደፊት ቀድሞ የሚጓዘው ግራኝና ጦሩ ራ ነቢያት ካለበት አስቸጋሪና ተራራማ ከሆነው ሥፍራ እንደደረሱ እመልክቶ በዚ ያም ሳያስቡት ራስ ነቢያትና ከርሱ ጋር ያሉት የደዋሮ ሹማምንት ተጠግተ ከወደ ላይ የደንገያ ናዳ እየለቀቁ ሲፈጁዋቸው ሲሉ እስላሞቹ የዛፍ ተገን እየያዙ ለጊዜው እንደ አልተጐዱ ግራኝና ጭፍሮቹ ሥፍራው ለፈረስ ውጊያ የማያመች ጠባብ ሆኖ ለክርስቲያኖቹ የተመቸ ስለሆነ እንግዲህ ከዚህ ሥፍራ ማለቃችን ነው በማለት እንደተጨነቁ ክርስቲያኖቹም "እስካሁን በልተሃል አሁን ግን መውጫ ዲህ ምን ይበጃል እያሉ ከፍ ያለ የዛቻ ድምፅ ማሰማታቸውንና እስላሞቹም ተጨንቀው እንግ ሔር ላይ ጣሉት የርሱን ድጋፍ ለምኑ . . . . . በዚህ ሥፍራ እኔና እናንተ እኩል ነን ችን የሚሞተው መንግሥት ሰማየት ይገባል የሚተርፈው በደስታ ይኖራል . . . » እንደ አላቸውና «በርቱ ጽኑ . . . . . . እግዚአብሔርን ፍሩ ታሸንፋላችሁ» የሚለ ውን ቃል በክፍል ፫ አንቀጽ ፰ - ፳፫ በቁራን የተጻፈውን እየጠቀሰ እንዳበረታታ ቸው ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ራስ ነቢያትና ጭፍሮቹ የናዳው በትር ምንም ያህል እስላሞቹን እንዳልጐዳ በተመለከቱ ጊዜ ቀርበው በጨበጣ ለመዋጋት ካሉበት ሥፍራ ተንቀ ነቁ ። በዚህ ጊዜ ታኪያ የሚባለው እጁና እግሩ ከዚህ በፊት በጦፋቱ ግራኝ ያስቆረ ጠው ይኸው መጡ እንዋጋ ብሎ ሲጮህ በነርሱ መካከል አንዱ ኡስማን የሚባል ባለጠመንጃ እርሱ ብቻ ነበርና እርሱ አነጣጥሮ የግራኛውን የክርስቲያን ጦር አለቃ መትቶ ሲጥለው እስላሞቹ ባንድ ድምፅ እየተጯጯሁ በክርስቲያኖቹ መካ ከል ተደበላልቀው ይዋጉ ገቡ ። 

(1) ይህ ፋኑኤል የተባለው ከዚህ በፊት በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. የተዋጋው ይሁን ወይም የሌላ ምክሼ ይሁን አይታወቅም ።

ጦርነቱም ኃይለኛ ስለነበረ ውጊያውም ስለጸናባቸው ክርስቲያኖቹ ሲሸሹ ራስ ነቢያትም ወደኋላው ተመልሶ ጭፍሮቹን «እንግዲህ ወዴት ነው የምትሸሹት ንጉሡ ፯፻ ፈረሰኞች ሆናችሁ ሐያ ፈረሰኞች እንዴት አባረሩዋችሁ ቢሉን ምን መልስ ይሰጣል» ቢላቸው እንደገና ተመልሰው ውጊያውን በኃይል እንዲቀጥሉ ራስ ነቢያትም "የወርቅ ተራራ" ከሚባለው ፈረሱ ላይ እንደተቀመጠ ሰይፉን መዞ ሲያዋጋ ግንባር ቀደም ሆነው ከሚዋጉት ከነፋራቃሃም ዓሊ ከነዓሊ ዋርዳይ ከነ ገራድ ናስር . . . . . ጋር በሰይፍ ተሟሙቆ ሲዋጉ በዚሁ ጊዜ ዓሊ ዋርዳይ ራስ ነቢያት አጠገብ ሆኖ ይዋጋ የነበረውን የጃዋቲር (ጋዋጢር ?) ሹም የነበረውን በሰ ይፍ አንገቱን ቢለው ጭንቅላቱ ከአካሉ ተለይቶ እንደ ወደቀ ፤ ቢሆንም ክርስቲያ ኖቹና እስላሞቹ አንድ ሰዓት ያህል ከተዋጉ በኋላ አሁንም እስላሞቹ አሸንፈው ክር ስቲያኖቹ እንደ ሸሹ ፤ ነቢያትም በፈረሱ ብርታት ለጥቂት አምልጦ ወደኋላው እንደሸሸ የዓረቡ ጸሐፊ ያመለክታል ።

ከዚሁ አያይዞ ግራኝ የድሉን የምሥራች ወደኋላ ከንዙና ከምርኮ ጋር ለቀረው ለወዚር አዶሌ ከላከ በኋላ ከነጭፍራው የበለው ግዛት በሆነው በጋፋት አዋዋልዳ ሠፈር ድንኳኑን አስተክሎ ተቀመጠ» ሲል ዓረብ ፋቂህ የራስ ነቢያትን ጦርነትና ፍጻሜ በዚህ ዓይነት ይጨርሳል (1) ።

መቼም ግራኝ አህመድ ባለፈው ጦርነት ደገልሃንን አርባ ሺመልን በተለ ይም ንጉሡ ነገሥቱን ማሸነፍ የቻለው ራስ ነቢያትን ማሸነፍ አያቅተውም ። ነገር ግን የዓረቡ ጸሐፊ በዚህ ከራስ ነቢያት ጋር በተደረገው ጦርነት ከክርስቲያኖቹ ብዙ ሲሞት ከኛ ወገን የሞተም የቆሰለም የለም የሚል ቃል ስለጨመረ ሁኔታውን ማመን ችግር ቢሆንም ማስተባበያ የሚሆን ስለዚህ ጦርነት በኛም ዘንድ በሌላም ዘንድ የተጻፈ ሰነድ ስለሌለ የርሱን ብቻ መቀበል ግዴታ ሆኗል ።

በዚህም ላይ ግራኝ ዋናውን የደጀን ጦር ወደኋላ ትቶ ወደፊት ቀድሞ ከጠባብ መንገድ ላይ ደርሶ በተቸገረበት ጊዜ እነራስ ነቢያት ከፊት መግጠም ብቻ ሳይሆን መውጫ መግቢያውን በሚያውቁት ባገራቸው ከኋላውም ጭምር አጥቂ ጦር አለ ማስከተላቸው አስገራሚ ነው ። ራስ ነቢያት ግራኝ ከነጦሩ ወደዚህ ምቹ ሥፍራ እንዲገባለት በዘዴ ስቦት ይሆናል ፡ ዳሩ ግን በዚሁ ጊዜ የተረፈና ወደፊት እየተዋጋ ሲተላለቅ ከምናየው ከብዙው ጦር አንድም ከግራኝ ከቀኝ ከኋላም የከበበ ያም ቢቀር በመላላክ አዲስ የርዳታ ጦር ሳይደርስለት መቅረቱ የስለላውና የግንኙነቱ በጠቅላላው የመንግሥቱ የወታደርነቱ ዝግጅት ደካማ እንደነበረ ያመለክታል ።

በግራኝ በኩል ግን ሁሉም የጦርነቱ አካሄድ የሚመራው በዘዴና በአእምሮ ጥናት ይመስላል ። ጦርነቱ ሊጀመር ሲል በመጀመሪያ ኡስማን የሚባለው ባለ ጠመንጃ አነጣጥሮ ተኩሶ የግረኛውን ወታደር ሹም ከጣለ በኋላ ባንድ የድምፅ ሁካታ እየተጯጯሁ ገብተው ጦርነቱን መጀመራቸው ከመጀመሪያው የውጊያ ወቅት ላይ የክርስቲያኑን ተዋጊ ልብ ለማሸበር ታስቦ የተደረገ መሆኑ አይጠረጠ ርም ።

(1) ዓረብ ፋቂህ . . . . . 131 - 146

በዓረብ ፋቂህም በኛም ታሪክ ነገሥት ውስጥ ከፖርቱጋሎቹ መምጣት በፊት በተለይ በዚህ ጊዜ አንድም ነፍጥ (ጠመንጃ) በክርስቲያኖቹ ጉራ መኖሩን ስለማ ይጠቅስ ምናልባት የጠመንጃ መልኩንም ዓይቶ ድምፁንም ሰምቶ የማያውቀ ውን ከጦርና ከጕራዴ በቀር በእጁ ያልያዘውን ባንዲት ጥይት ተዘርስና እመታት ተከላካዩን ወታደር አስበርግጎ ከዚያ ደግሞ በትኩሱ ጸንቶ በሰይፍና በጕራዴ በመ ዋጋት ከማሸነፍ ደርሶ ይሆናል ። እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ጠመንጃዋ አንድ ብቻ ዋን ብትሆንም የመዠመሪያዋ ጥይት አንዱን ተዋጊ እሲቃ ከጣለች በኋላ ሌሎቹ ጥይቶች ሌሎቹን ተዋጊ ሹማምንት እየመቱ ለማቁሰል እንደማይቦዝኑ የታወቀ ነው ።

## ምዕራፍ ፵፪

## የሱልጣንና የይማም ልዩነት - የሱልጣን ኡመር ዲንና የግራኝ አህመድ ጠብና ዕርቅ (፲፰፻፹፱ ዓ. ም.)

በክርስቲያኖቹ ቤተ መንግሥት እንዳለው ሁሉ በእስላም አገሮችም የቤተ መንግ ሥትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ዘንድ ልዩ ልዩ ደረጃና ስያሜ አለ ። ያንዱ እን ርም ከሌላው በመጠኑ ሳይሾይይ አይቀርም ። የሆነ ሆኖ በዚሁ መጽሐፍ አልፎ አልፎ ሲጠቀስ የምናነበው የሥልጣን ደረጃ ይነስ ይብዛ ከሐጅ የሱፍ ያገኘሁት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

፩ኛ. ሱልጣን — ባለሥልጣን ቁሣር ወይም ንጉሥ ነው ። እርሱም ለሁሉ የበላይ ነው ።
፪ኛ. ይማም — የሃይማኖትና የሥጋዊ ሥልጣን ደርቦ የሚመራ የሚስ ብክ ሕዝብ ሊከተለው የሚገባ ፤
፫ኛ. ወዚር — ሚኒስትር ወይም አማካሪና አስተዳዳሪ ፤
፬ኛ. አሚር - የጦር መሪና አገረ ገዥ ወይም አዛዥ ፤
፭ኛ. ሼክ — መምህር (አረጋዊ) ፤
፮ኛ. ሸሪፍ — ከነቢዩ ከመሐመድ የሚወለድ ፤
፯ኛ. ቃዲ — ዳኛ ፤ ፈራጅ ፤
፰ኛ. ሐጂ — ሚካን ተሳልሞ የመጣ ፤
፱ኛ. ሙእዝዚን — ለጸሎት ተሰብሰቡ ብሎ በጩኸት የሚለፍ ፤
፲ኛ. አውራይ — ከበለው ወገን የሚወለድ (ልጅ እገሌ እንደሚባል) . . . .

በአሁኑ ጊዜ በግራኝ አህመድ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ እንደ አዶሌ ያሉ የወዚርነት ማዕርግ ያላቸው ቍጥራቸው እስከ አራት የሚደርስ የአሚርነት ማዕ ርግ ያላቸው ቍጥራቸው ወደ አሥር የሚጠጋ ሌሎችም ሼኮች ፣ ቃዲዎች ፣ ሸሪ ፎች በየሥፍራቸው ተደልድለው ግራኝ አህመድ በሚሰጠው አሳብና ትእዛዝ እየ ተመሩ ያከናውናሉ ። ከነዚህ መካከል ደግሞ በነርሱ በሱማሌና በአዳል በኛም

ISIC

በዓረብ ፋቂህም በኛም ታሪከ ነገሥት ውስጥ ከፖርቱጋሎቹ መምጣት በፊት በተለይ በዚህ ጊዜ አንድም ነፍጥ (ጠመንጃ) በክርስቲያኖቹ ጐራ መኖሩን ስለማ ይጠቅስ ምናልባት የጠመንጃ መልኩንም ዓይቶ ድምፁንም ሰምቶ የማያውቀ ውን ከጦርና ከጐራዴ በቀር በእጁ ያልያዘውን ባንዲት ጥይት ተዙስና አመታት ተከላካዩን ወታደር አስበርግጎ ከዚያ ደግሞ በትኩስ ጸንቶ በሰይፍና በጐራዴ በመ ዋጋት ከማሸነፍ ደርሶ ይሆናል ። እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ጠመንጃዋ አንድ ብቻ ዋን ብትሆንም የመዠመሪያዋ ጥይት አንዱን ተዋጊ አሲቃ ከጣለች በኋላ ሌሎቹ ጥይቶች ሌሎቹን ተዋጊ ሹማምንት እየመቱ ለማቁሰል እንደማይበዙ የታወቀ ነው ።

ምዕራፍ ፵፪
የሱልጣንና የይማም ልዩነት - የሱልጣን ኡመር ዲንና የግራኝ አህመድ ጠብና ዕርቅ (፲፰፻፹፱ ዓ. ም.)

በክርስቲያኖቹ ቤተ መንግሥት እንዳለው ሁሉ በእስላም አገሮችም የቤተ መንግ ሥትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ዘንድ ልዩ ልዩ ደረጃና ስያሜ አለ ። ያንዱ አገ ርም ከሌላው በመጠኑ ላይ[illegible]ይ አይቀርም ። የሆነ ሆኖ በዚሁ መጽሐፍ አልፎ አልፎ ሲጠቀስ የምናነበው የሥልጣን ደረጃ ይነስ ይብዛ ከሐጅ የሱፍ ያገኘሁት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።


፩ኛ. ሱልጣን — ባለሥልጣን ቄሣር ወይም ንጉሥ ነው ። እርሱም ለሁሉ የበላይ ነው ።
፪ኛ. ይማም — የሃይማኖትና የሥጋዊ ሥልጣን ደርቦ የሚመራ የሚስ ብክ ሕዝብ ሊከተለው የሚገባ ፡
፫ኛ. ወዚር — ሚኒስትር ወይም አማካሪና አስተዳዳሪ ፡
፬ኛ. አሚር - የጦር መሪና አገረ ገዥ ወይም አዛዥ ፡
፭ኛ. ሼክ — መምህር (አረጋዊ) ፡
፮ኛ. ሸሪፍ — ከነቢዩ ከመሐመድ የሚወለድ ፡
፯ኛ. ቃዲ — ዳኛ ፡ ፈራጅ ፡
፰ኛ. ሐጂ — ሜካን ተሳልሞ የመጣ ፡
፱ኛ. ሙአዝዚን — ለጸሎት ተሰብሰቡ ብሎ በጩኸት የሚለፍ ፡
፲ኛ. አውራይ — ከበለው ወገን የሚወለድ (ልጅ እገሌ እንደሚባል) . . . .

በአሁኑ ጊዜ በግራኝ አህመድ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ እንደ አዶሌ ያሉ የወዚርነት ማዕርግ ያላቸው ቍጥራቸው እስከ አራት የሚደርስ የአሚርነት ማዕ ርግ ያላቸው ቍጥራቸው ወደ አሥር የሚጠጋ ሌሎችም ሼኮች ፡ ቃዲዎች ፡ ሸሪ ፎች በየሥፍራቸው ተደልድለው ግራኝ አህመድ በሚሰጠው አሳብና ትእዛዝ እየ ተመሩ ያከናውናሉ ። ከነዚህ መካከል ደግሞ በነርሱ በሱማሌና በአዳል በኛም

# የወላስሞች የዘር ግንድ

[illegible]

[illegible]




[illegible]

ISIC

በኩል በደዋሮ ፣ በባሌ ታላላቅ አውራጃ ውስጥ የገራድነት ሹመት ያላቸው የደዋሮ ገራድ የባሌ ገራድ የወጅ ሄገኖ እየተባሉ የሚሾሙ ይኸም ሹመት እስከ ዛሬ ድረስ የነዚያ ተወላጆች ሲጠሩበት ይኖራሉ ።

አሁን በግራኝ አህመድና በሡልጣን ኡመር ዲን መካከል የተነሣውን ጠብ ከመመልከታችን በፊት በሁለቱ መካከል ያለውን የዘርና የሥልጣን ልዩነት እንመልከት ። በሐረር የሡልጣንነት ሥፍራ የሚቀመጠው በአዳሎችና በሱማሌዎች ዘንድ እንደ አንድ ንጉሥ የሚቆጠር ነው ። እርሱም በሸዋ እገሌ ከላይ የልብነ ድንግል የያዕቆብ የነጋሢ ልጅ ከታች የሣህለ ሥላሴ ዘር እንደሚባለው ፤ ኡመር ዲንም ከላይ የወላስማ ዘር ከታች የሰዓዲን ልጅ ይባላል ። አገሩም በጠቅላላ በሐረር ሡልጣናዊ ግዛት ውስጥ የሚገኘው የሱማሌና የአዳል አገር በመላው አዳል ወይም ሐረር በመባል ፈንታ የሰዓዲን አገር ይባላል ። ይኸም ሸዋ የስብስቤ የአምሐየስ አገር እንደሚባለው ነው ።

ኡመር ወላስማ ከዓረብ አገር (በ፲፫ኛው መቶ ዓ.ም.) ወደ ይፋት መጥቶ ባላባትነቱን እስከ አዳል ድረስ ባሉት የእስላም ወገኖች ላይ የመሠረተ የዓረብ ተወላጅ መሆኑን የርሱ ልጆች ደራደር ፤ ሐቀዲን የልጅ ልጆቹ እነገማልዲን (ጋማል አድዲን) በተለይም የገማል ዲን ወንድም የማንሱር የልጅ ልጅ ሰበርዲን (ሳብር አድዲን መሐመድ) ካፄ ዓምደ ጽዮን ጋር በየጊዜው መዋጋታቸውን ባለፈው ጠቅሰናል ። የጦርነቱም ግዕዝኛ ጽሑፎችን በተለይ ሰበርዲንን «ሰብረዲን የሚባለው የከሐዲዎቹ ንጉሥ በመላ ኢትዮጵያ ላይ እነግሣለሁ ብሎ በጌታው በዓምደ ጽዮን ላይ ተመካ . . . . .» እያለ ይዠምርና የጦርነቱን ሐተታ ይቀጥላል (1) ።

ካፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር ተዋግቶ የሞተው አርዌ በድላይ (በድላይ ሺሃብ ኤድዲን አህመድ) ለነስረዲን አምስተኛ ትውልድ ለኡመር ወላስማ አሥረኛ ትውልድ ነው ። የአርዌ በድላይ ልጅ መሐመድ ቤን በድላይ ባፄ በእደ ማርያም ጊዜ ከገበረ በኋላ የርሱ ልጅ ሶሌይማን አህመድ ተዋግቷል (2) ።

በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ግድም ይኸውም ማለት ባፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት በአቡበከር ሡልጣንነት ጊዜ የይፋት ወላስሞች መቀመጫ ከተማቸውን ከይፋትና ከዳካር ወደ ሐረርጌ አዛወሩ ። ከይፋት ዠምሮ በአዳል በሱማሌ ምንም ዓይነት ቀንደኛና የታወቀ መሪ ተዋጊ ቢነሣ እነዚህ የወላስማ ዘሮች እንደ ደንበኛ የነጋሢ ዘር በመቆጠራቸው ከዙፋናቸው አይወድቁም ። ማኅፉዝና ዓፄ ልብነ ድንግል በ፲፭፻፰ ዓ.ም. የተዋጉለት የጦርነቱን አስጊነት በመመልከት «እኔ እዚሁ ተዋግቼ ለመ ሞት ቆርጫለሁ አንተ ግን በፈረስ አምልጥ» ብሎ አብሮት ለነበረው ለሡልጣን መሐመድ የመከረው እንደተለመደው ነጋሢውን ከሞት ለማዳን ሲል ነው ።

ይህ ያመለጠው መሐመድ ለአርዌ በድላይ አራተኛ ትውልድ ነው ። የመሐ

(1) አዕበየ ርእሶ ንጉሠ ዕልዋን ዘስሙ ሰብረዲን ወተመክሐ ላዕለ እግዚኡ ዓምደ ጽዮን ወይቤ እከውን ንጉሠ ላዕለ ኵሉ ምድረ ኢትዮጵያ . . . . . እያለ ይዠምርና የጦርነቱን ሁኔታ ይቀጥላል ።
የዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ዢል ጔሩሾ ያሳተመው ገጽ 280

(2) የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 35 ፥ 46 ፥ 48

ISJC

መድ ልጁና ተከታዩ ሱልጣን አቡበከር ግራኝ አቤቱ፡ ያደገውን ገራድ አቡንን ከገደለ ወዲህ በግራኝና በሱልጣን አቡበከር መካከል የነበረውን ጦርነት በግራኝ አህመድ አነሣሥ ምዕራፍ ፴ ላይ እንብበናል ። አቡበከር ግራኝን ለመግደል እየፈለገ ሳይሆንለት ቀርቶ ግራኝ አቡበክርን አስገድሎ በርሱ ፈንታ ራሱ መንገሥ ስለማይችልና ዘሩ ስለማይፈቅድለት ከዚያው ከወላስማ ሥርወ መንግሥት የወረደ የነጋሢ ዘር በመሆኑ የሚቹን የአቡበክርን ወንድም ኡመር ዲንን ሱልጣን እንዳደረገው ዓረብ ፋቂህ (በባሴት ትርጉም) በመጽሐፉ የገለጸውን ከዚህ በፊት አንብበናል (1) ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ግራኝ አህመድ በግብርና በምርኮ ሀብት ሲጣሉ ወደፊት የምናነበው ከዚሁ ከኡመር ዲን ጋር ነው ።

የኡመር ዲን የሱልጣንነትና የግራኝ አህመድ የይማምነት ሥልጣን በጉንደር (፲፭፻፵፯ - ፲፭፻፷፩ ዓ. ም ) ከነገሡት ካፄ ኢዮአስና ከእንደራሴያቸው ከራስ ስሑል ሚካኤል ጋር ይመስላል ። ከላይ ከልብነ ድንግልና ከታች ከፋሲል የሚወለዱት ዓፄ ኢዮአስ ከአባታቸው ከዓፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ቀጥለው በ፲፭፻፵፯ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ ነግሠው ሲያስተዳድሩ ዋናውን የሥልጣን ሥራ ጨብጠው በንጉሣቸው ላይ ተጭነው ለሸረት የማይመቹ ሆነው አገሪቱን ይገዙ የነበሩት ኃይለኛው ራስ ስሑል ሚካኤል ነበሩ ። በእንደራሴያቸው መጫን ያለፈቃዳቸው የዳሞቱ ፋሲል የሸፈተ ጊዜ በገሀድ ራስ ስሑል ሚካኤልን እንዲዋጉ ልከው ውስጡን ደግሞ ፋሲል በርትቶ ራስ ስሑል ሚካኤልን እንዲገድል አሽከራቸውን ልከው ይኸው ሥራቸው በኋላ ተገልጾ ንጉሡ በራስ ስሑል ሚካኤል ሥልጣን ተፈርዶባቸው በነደጃች ነሬ ልጆች እጅ በሻሽ ታንቀው ሞቱ (2) ።

ግራኝ አህመድም አቡበክርን አስገድሎ ወንድሙን ኡመር ዲንን እንዳነገሡ ሁሉ በዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ራስ ሚካኤልም ዓፄ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቀው ካስገደሉ በኋላ ያፄ ኢዮአስን አያት የበካፋን ወንድም እጀ ቆራጣ ዮሐንስን ተግዘው ከሚቀመጡበት ከወህኒ አምባ አውርደው አነገሡዋቸው (3) ። ዓፄ ዮሐንስ በመገርመሪያ ንግሣቸው ጊዜ ደስ ብሏቸው ይከማ የነጋሢነት ሥልጣን ማጣጣም እንደጀመሩ እያደር ግን የራስ ሚካኤል ተጫኝነት ስለከበዳቸው በመካከላቸው ቅርታ ሊገባ ቻለ ። ከዕለታት አንድ ቀን ራስ ሚካኤል «አብረን ሄደን ፋሲልን እንውጋ» ቢሏቸው በወህኒ አምባ ሲኖሩ ከጸሎትና ከመጻሕፍት ምርመራ በቀር ጦርነት ስለ አልለመዱ ወይም የጦርነቱን ምክንያት ስለአልተቀበሉት «ወደ ጦር ግንባር መሄድ አልፈልግም ካልሆነም ወደ ነበርሁበት ወደ ወህኒ አምባ መልሰኝ» ብለው በዚሁ ተጣልተው በእጅ አዙር እንደራሴው ንጉሡን አስገደሏቸው ። አሁንም በዚሁ ዓይነት ግራኝ ያነገሠው ሱልጣን ኡመር ዲን በግብርና ፤ በምርኮ መልሶ ከግራኝ ሲጣላ ታሪክ በያለበት በየጊዜው ሲደጋገም እንመለከታለን ።

ሱልጣን ማለት ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ትርጓሜው "ሥልጣን ቻሎት"

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 32 - 33
(2) የኢያሱና የኢዮአስ ዜና መዋዕል ጉይዲ ያሳተመው ገጽ 251
(3) የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ ምዕራፍ 67 - 69

ሲሆን ይኸን የማዕርግ ስም የያዘ ገዥ ያው ባገራችን ንጉሥ ማለት ነውና ብዙ ሐተታ መጨመር የሚያስፈልገው አይመስለኝም ። ነገር ግን ግዛቱ ከማሮክ እስከ ፋርስ ፤ ከፋርስ እስከ ነምሳ ጫፍ የሰፋው ታላቁ የቱርክ ንጉሠ ነገሥት ሱልጣን ሲባል የትንሹም የሐረርጌ ወይም የአዳል ገዥ ይኸንኑ የሱልጣንነት ስም ይጠራበታል ። በኛም ዘንድ ያንዱ አውራጃ ጌታ የጅማው አባ ጅፋርም በዚሁ ይዞታ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይጠሩበት ነበር ። ነገር ግን የቱርኩ ሱልጣን «ንጉሠ ነገሥት የምዕራብና የምሥራቅ ገዥ የግሪክ ፤ የፋርስ ፤ የዓረብ . . . . . . የኢየሩሳሌምና የሜካ የሆንግሪና የብዙ አገሮች መስፍን . . . . .» እያለ የሚጠራበት እርእስቱ ብቻ ግማሽ ገጽ ይፈጃል (1) ።

ግራኝ አህመድ ግን በአንሣሱ ምዕራፍ ፰፰ ላይ እንደተገነዘብነው ይማም እንጂ ሱልጣን እንዳይባል ፡ ሐበሻን ሊገዛ የሚችለው በይማምነት እንጂ በሱልጣንነት አለመሆኑን ትንቢት ባለበት ውሳኔ አዋቂዎቹ ስለአስጠነቀቁ እኛ ግራኝ አህመድ የምንለው በዓረቦቹ ዘንድ ይማም አህመድ ይባላል ። በዚሁ ምክንያት የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ይማም አህመድ ይለዋል ።

ሱልጣንነት እንደ ነጋሢ ልጅ በዘር ሲወራረስ ይማምነት ግን ጠባዩና ችሎታው ታይቶ ላንድ ሰው በምርጫ የሚሰጥ የሃይማኖትና ያስተዳዳሪነት ሥልጣን የያዘ ነው ። ቀድሞ የባግዳድ ከሊፋዎች (ያው የሱልጣን ያህል ችሎታ ያላቸው) ይማምነትን ደርበው ይይዙ ነበር ። የየመን ገዥዎች እስከ ቅርብ ጊዜ በዚሁ በይማምነት ይጠራ ነበር ። የሆነ ሆኖ ይህ ግራኝ አህመድ የያዘውን የይማምነትን ማዕርግ ለማግኘት ፡

ሀ. በሞራል ከሁሉ በላይ ሆኖ የሐቅ መንገድ ማሳየት ።

ለ. የቀረበለትን ጉዳይ ሁሉ ለመወሰን በቂ ዕውቀት ማግኘት ።

ሐ. አይማጭነቱ እንጋገሩ አስተያየቱ ያልተንደለ ።

መ. የሰውነቱ መለያልይና አካሉ በሙሉ ጉድለት የሌለበት ።

ሠ. ያገር ጉዳይ ለመምራት በቂ ልማድና ፍርድ አጠባበቅ ያለው ።

ረ. የእስላምን መብት ለመጠበቅ ጠላትን ለመዋጋት ድፍረትና ብርታት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል (2) ።

ስለዚህ ከወላስማ ዘር የወረደው ኡመር ዲን በሐረር ዙፋን ሱልጣን ሆኖ ሲገዛ ግራኝ ይማም ተብሎ እንደ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የአገር መሪ ሆኖ ያስተዳድራል ማለት ነው ።

ግራኝ አህመድ ለስሙ ከሱልጣኑ በታች ይምሰል እንጂ በያዘው መንፈሳዊና ሥጋዊ ሥልጣን የተነሣ በመፈራት ከሱልጣኑ በላይ ሆኗል ። በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ ግንባር የወላስማን ሱልጣኖች እነሰበርዲንንና እነሐቀ ዲንን እነ ማኅፉዝንም ሲያጠቁ ሲገዙ ሲያስገብሩ በኖሩት የክርስቲያን የጦር አለቆች ላይ በተለይም በተ

(1) Soliman le Magnifique-trad. CUIMLLIMIM ምዕ. XIII ገጽ 216

(2) ISLAM MEDIEVAL የሚባለውን ፕሮፌሰር ግሬንቦም CRUNBAUM መጽሐፍ ገጽ 173 - 174

ISIG

ከበረውና በገናናው ንጉሠ ነገሥት ላይ በሽምብራ ኩሬ ድል አድራጊነትን ስላገኘ
ከኢትዮጵያ በወሰደው የምርኮ ሀብት በወዲህ ኤሚሮቹን ቃዲዎቹንና ሼሆችን
ከቀይ ባሕር ማዶ ያሉትን የዘቢድን የአደንን የጀዳህን ሱልጣኖች ስለአከበረ በሱል
ጣኑ ሰፊ ግዛት ውስጥ ስመ ጥር ስለሆነ ቀድሞ የፈረንሳዊ ንጉሥ ሻርል ፯ኛ ዣን
ዳርክ በእንግሊዞች ላይ ባገኘችው አሸናፊነት የተነሣ እንደተመቀኘው ዓይነት
አሁንም ሱልጣን ኡመር ዲን በየጊዜው ስለሚያገኘው ድልና የምርኮ ሀብት በግ
ራኝ ላይ ቅናትና ምቀኝነት እንደሚያድርበት የታወቀ ነው ።

በሱልጣንነቱ ዙፋን ላይ ተቀምጦ በየጊዜው በየሰዓቱ የግራኝን የአሸናፊነት
ዝናና ክብር መስማትና ማየት ሸክም ስለሆነበት ምናልባት በፈጠጋር በደዋሮ በሽ
ምብራ ኩሬ የተዋጋለት እርሱም ባንዳንዱ የጦርነት ሜዳ በገሀድ ተካፋይ መሆኑ
ባይቀር ውስጡን ግን ከግራኝ ከባድ ሥልጣን ለመገላገል በክርስቲያኖቹ ኢትዮ
ጵያውያን እጅ ቢማረክ ወይም ቢሞት የሚጠላ አይመስልም ። የኛ መንግሥት ግን
ይኸን በመሳሰለው ሁኔታና ጥላቻ ሊጠቀምበት አልቻለም ። ሊጠቀምበትም ያል
ቻለው በነርሱ መካከል የሚሆነውንና የደረሰውን ለማወቅ የሚረዳው የስለላ ድር
ጅት ለማቆም ከነዚያ ሕዝብ ጋር ግንኙነት ለማግኘት አቅሙ ስላጠረ ይመስላል ።

ነገር ግን ግራኝ አህመድ በወዲህ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገውን ጦርነት
ጂሀድ ቅዱስ ጦርነት አሰኝቶ ብዙ ሕዝብና ሹማምንት አነቃቅቶ የተነሣ በመሆኑ
በመደገፍ ፈንታ ይኸን ቅዱስ ጦርነት ሱልጣኑ የተቃወመ እንደሆነ በሕዝብ ዘንድ
እንዳያስጠላው በመሥጋት በግድም በውድም ጦርነቱን እዚያው ሐረር ተቀምጦ
በማናቸውም መደገፍ ግዴታ ሆኖበታል ። ከዚህም አልፎ በዋናው በሽምብራ ኩሬ
ጦርነት ተካፋይ እንደነበረ ባለፈው አንብበናል ።

ሆኖም በሃይማኖትና በቅዱስ ጦርነት በደሉኝታና በወገንነት ምክንያት በሁ
ለቱ መካከል ያለው የተዳፈነ የእሳት ጠብ አልፎ አልፎ ቦግ ከማለት አላቋረጠም ።
ግራኝ አህመድ በአሁኑ ጊዜ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ባለፈው ካገኘው ምርኮ በቀር ከደ
ዋሮ ከነራስ ነቢያት የማረከውን ብዙ ሀብት ይዞ እንደገና ወደ ሐረር ሲመለስ በሁ
ለቱ መካከል በግብርና ፥ በምርኮ ሀብት የተነሣ ጠቡ ተቀስቅሶ ነበር ። ነገር ግን
ቅዱሱን ጦርነት ለመቀጠል ኅብረት አስፈላጊ መሆኑን በማስረዳት በሁለቱ ጠበ
ኞች መካከል ሼኮቹ እየገቡ ጠቡ ሁልጊዜ ሳይከር ስላስታረቋቸው ግራኝ አህመድ
የወደፊት ወረራውን እንደልቡ ለማከናወን ችሏል ።

በአሁኑ ጊዜ (፲፭፻፳፪ ዓ. ም.) በሱልጣን ኡመር ዲንና በግራኝ መካከል የደረ
ሰው የዕርቅና የጠብ ሁኔታ ራሱ ዓረብ ፋቂህ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዓይነት እየተረከ
ያመጣዋል ። «. . . . . ይማም . . . . . ከኤዲር (ደፋትና ደዋሮ ጉን ያለ አገር) ወደ
ሐረር ተመለሰ . . . . . ። በዚያም ሳለ አገሪቱን ለሚያስተዳድሩት ለአቡበከር ወን
ድም ለሱልጣን ኡመር ዲንና ለኤሚሮቹ እንደዚህ አላቸው ። እስላምን ከፍ ስላደ
ረገና ኃይል ሰጥቶ ስላከበረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ። አባቶቻችን አድርገ
ውት ፤ አግኝተውት የማያውቁትን ከክርስቲያኖች ላይ ምርኮና ሀብት አገኘን ።
ይኸም ሀብት ለኑሮአችንና ለጦር መሣሪያ መግዣ ይበቃናል ። ካገር የሚወጣውን

ISIC

ግብር ግን ስምንት ላይ ይከፈላል አለ . . . . (1) ።

ሱልጣኑና ኤሚሮቹ ከፍርሃት የተነሣ ሳይቃወሙ እሺ ብለው ተቀበሉት ። እርሱም ግብር ካገር ላይ የሚያወጡትን ሠራተኞቹን ላከ ፡ ወታደሩንም "በያገራ ችሁ ግቡ ፈረሶቻችሁን መግቡ ፤ ሁለተኛ መጥቼ ለጦርነት እስክልካችሁ ድረስ ተጠንቅቃችሁ ተዘጋጅታችሁ ተቀመጡ ። እኔ ወደ ዘርባህ ሄጄ ሱማሌዎቹን እስ ማምቼ ወታደር ሰብስቤ ወደ እናንተ እመለሳለሁ ።" አላቸውና ወታደሮቹ እሺ ብለው በያገራቸው ገቡ ። ይማምም ወደ ዘርባህ ሄደ ። በዚህ መካከል ሱልጣን ኡመር ዲን ከኤሚሮቹና ከወዚር ኑር ፤ ከገራድ አህሙሽ ፤ ከቀጢን አቡበከር . . . . . ጋር ስለግብሩ ነገር ተነጋገረ ። "ይማም ከየግዛታችን ግብር እንዳንቀበል ሊከለክ ለን ነው ከጥንት ከሳዓድ ዲን ዠምሮ የነበረንን ግብር ሊሠርዝ ፈልጓል ፤ እኛ ግን አንተውም ፤ በኛ ላይ የመጣ እንደሆነ እነሱን ይዘን እንዋጋለን ፤ ያለዚያ ግን አገሪ ቱን ለኛ ትቶ እርሱ ሚስቱን ድል ወንበራን ይዞ ቢፈልግ ወደ ዓረቢያ ያለዚያ ወደ መካ ይሂድ ፤ እንፈልገውምና ሁለተኛም ወደ አገራችን አይመለስ" እያሉ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩና ሐረር የተዋቸውን አሽከሮቹን ሌሊት ወግተው የጦር መሣሪ ያና ፈረሶቻቸውን ቀሟቸው ። በዚያን ጊዜ ሕግ አዋቂው አቡበከር ኤል አልሹኒ ወደ ሱልጣኑና ወደ ኤሚሮቹ ሄዶ "ምንድነው ይህ የምትሠሩት የከፋት ሥራ" ብሎ ጠየቃቸው ። እነርሱም "ደግ አድርገናል ፤ ሄድና ለይማም ሌሎቹን ፈረሶችና የጦር መሣሪያ እንዲያስረክበን ንገረው ። እርሱም ከነሚስቱ ወደ ፈቀደበት ይሂድ እንጂ ወደኛ አይምጣ ። የመጣ እንደሆነ እንገለውና ከርሱ ጭቅጭቅ እንገላገላ ለን" ብለው መለሱለት ።

ISIC

ከዚህ በኋላ አቡበከር ወደ ይማም ሄደና የተላከውን ደብዳቤ ሰጠው ። እር ሱም በዘርባህ አገር ሆኖ የሆነውን ሁሉ ነገር ሳያውቅ ከገበሬዎቹ ጋር "ይኸን አድ ርጉ ይኸን አታድርጉ" እያለ በጸሞና ሲነጋገር ነበርና ደብዳቤውን ከአቡበከር ተቀ ብሎ አንብቦ ነገሩን ሲረዳው "ደህና ነው ከፋት ካሰቡ ያሰቡትን ይፈጽሙ ፤ እኔም አገሩን ትቼላቸው እሄዳለሁና ይኸንኑ ተመልሰህ ንገራቸው" አለው ። በዚህ ጊዜ ሁሴን ቤን አቡበከር ኤል ጋቱሪ ተነሣና "እንደዚህ አይሆንም ጦርነት ፈልገው እንደሆነ የሲምን የሱማሌን የጊሪን ፤ የሀብር ማጋዲን ፤ የሀርላህን ነገድና የተበታ ተነ ወታደር ሰብስበን እንወጋቸዋለን እንጂ የፈቀዱትን ያድርጉ ብለን አገሪቱን አንተውላቸውም" ብሎ ለይማም ሲናገር የቀሩትም እዚያ የነበሩት እነ ኤሚር ዓሊ ፤ እነአውራይ አህመድ ዲን እነ ገራድ ዘሀርቡይ መሐመድ . . . . . . እነ አብድ ኢን ናስር እነአህመድ ጎይታ . . . . . እየተነሡ "የሁላችንም አሳብ እንደ ሑሴን አቡበከር ነው" ብለው ተናገሩ ።

ከዚህ በኋላ ይማም አህመድ ከዘርባህ ተነሥቶ የአራት ቀን ጉዞ አድርጎ ጊና ሲር ደርሶ ከዚያ ጫት እሞላበት ዊልካም (ውልቃም ?) እሚባለው አገር ደረሰ ። ይኸም አገር ከሀበሻም ከትግሬም የሚመጡ እስላሞች የሚቀመጡበት ሥፍራ

(1) እስምንት ላይ ተከፍሎ ለደሀ ፣ ለአሥረኛ . . . . ይሰጥ ለማለት ይሆን እንጂ ነገሩ ግልጽ አይደለም ።

ነው ። ከታመኑት ኤሚሮች ውስጥ መገመሪያ መጥቶ የተገናኘው ገራድ ናስር ነው ። ሱልጣን ኡመር ዲን የይማምንና የጦሩን መምጣት ሲሰማ ሸሪፎችንና ሸኮችን (ቀሳውስት) እኔንና ይማምን አስታርቁን ብሎ ጉትጉቶ ላካቸው ። እነርሱም ወደ ይማም መጥተው ነገሩት ። እርሱም እሺ ብሎ ከታረቀ በኋላ በደስታ በድል አድራጊነት ሐረርጌ ገባ ። በዚህ መካከል ሂራቡ የሚባል የመሬሃን (1) የሱማሌ ባላባት የሱልጣን ኡመር ዲንን አሽከር ስለገደለ ይማምና ሱልጣኑ እርሱን ሊወጉ ሄዱ ። በኋላ ግን የደም ዋጋና ያሉትን ፈረሶች አስረክቦ ከመወጋት ዳነ . . . . . ከዚህ በኋላ ሱልጣኑ ወደ አገራችን ወደ ሐረር እንመለስ አለ ፤ ይማም ደግሞ ባሌን እንውጋ አለ ፤ ሱልጣኑ አንተ ያንድ ክፍል ጦርና የቀሩትን ሹማምንት ይዘህ ሂድና ተዋጋ እኔ ግን ወታደሬ ደክሚልና ወደ ሀገሬ እመለሳለሁ ብሎት ወደ ሐረር ሔደ ። ይማም ከነጦሩ በኪዳድ ሠፈረ ። በዚያም ሳለ ሹማምንቱና ወታደሩ ስንቅ የለንም እንደምን ወደ ባሌ እንዘምታለን ብለው ጠየቁት ። እርሱም ካገር ጌቶችና ከባላገር ላይ አስመጥቼ እሰጣችኋለሁ አላቸው ። ከዚህ በኋላ ይማም የአላዊ ቤን ዓሊን . . . . ሌሎችንም ሸሪፎች ቅዱስ ጦርነት የምናደርግበት ስንቅ ስጡን ፡ እርዱን ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም እሺ ብለው ሰጡት ። . . . . . ከዚያ ቀጥሎ ኪዳድን ትተው እስላሞቹ ወደ ባሌ ተጓዙና ደለፋይ ጀልብ (ገለብ ?) ከሚባል የእስላሞች አውራጃ ደረሱ። በዚህ ወረዳ ያሉት ሸሪፍ ሐኪም ቤን ኡመር . . . . . ሸሪፍ ሸክ ቤን አብደላ ፣ ሸሪፍ ሐኪም ቤን ኤዝዘፋይ . . . ISIC ይማምን ከነጦሩ ተቀብለው አስተናገዱት» (2) ።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሱልጣን ኡመር ዲን ካንዳንድ ኤሚሮች ጋር ሆኖ ሁል ጊዜ አበሻን እንውጋ እያለ ያስቸገረውን ግራኝን ለመጣልና ከርሱ ጭቅጭቅ ለመገላገል ባደመበት ጊዜ ከርሱ ጋር የነበረው ሁሴን ኤል ጋቱሪ አገሪቱን ትተንላቸው እንሂድም ። የጊሪን ፤ የሱማሌን . . . . . . ነገድ ይዘን እንወጋቸዋለን ሲል ግራኝና ወገኖቹ በሱማሌ ነገድ ላይ የጸና እምነት ነበራቸው ማለት ነው ። የዚህም ምክንያት ባንድ ወገን በሆባት የሚገኘው የመለሳይ ነገድ የግራኝ ወገን ስለሆነ ከሱማሌ ጋር የነገድ ዝምድና እንዳላቸው ይታወቃል ። ዓረብ ፋቂህ የሱማሌን ነገድ ለየብቻ እየዘረዘረ ሲያመጣ በዚያው ውስጥ የግራኝን ነገድ የመለሳይን በዚያ ውስጥ ይጨምረዋል (ገጽ ፹፬ - ፩፻፲፩ - ፩፻፵ . . . . . .) ። በዚህም ላይ የሱማሌዎች መሪ ገራድ ማታን የግራኝን እኅት ያገባ እማቹ ስለሆነ ግራኝን ከሱማሌዎች ጋር የበለጠ አቀራርቦ አዛምዶታል ። ይኸም በምዕራፍ ፳፱ የጻፍነውን የሚያጸድቅ ነው ።

አድመኞቹ "ቢፈልግ ሚስቱን ድል ወንበራን ይዞ ወደ ዓረብ አገር ወይም ወደ መካ ይሂድ" ያሉትን መሠረት በማድረግ ግራኝ አህመድ ዘሩ ዓረብ ይሆን የሚሉ ጥርጣሬ ባንዳንድ ጸሐፊዎች ዘንድ ሊያሳድር ችሏል ። ነገር ግን ከሹመቱ የተዋረደ ይማም ሊሰደድበትና ሊኖርበት የሚገባው የመሐመድ መቃብር ያለበት

(1) መሬሃን በውጋዴንና በሚጁርቲኒ መካከል የሚገኝ በፍጥረቱ ጦረኛ የሆነ ነገድ ዓረብ ፋቂህ ገጽ 35 - 36

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 146 - 154

መካ በመሆኑ እንጂ የዚያ አገር ተወላጅ በመሆኑ አይደለም ። ይኸም በኛ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ሰው ሲያረጅ ወይም ከሹመት ተዋርዶ ዓለም በቃኝ ብሎ ገዳም እንደሚገባ ወይም ወደ ኢየሩሳሌም መሄድና በዚያ መቀበርን እንደሚመኘው ማለት ነው ። ይሁን እንጂ በዚህ መካከል የምንመለከተው ሱልጣኑ ኡመር ዲንና ግማሹ ክፍል ጦርነት በቃን ያገኘነውን እንደያዝን ሕዝባችንን እንደተለመደ እያስገበርን በሰላም ባገራችን እንኑር እያለ ሲመኝ ግራኝ ባገኘው የመሪነት ሥልጣን እየተጫነ እስካሁን ባገኘው የአሸናፊነት ዝና እየተመረኰዘ ሁሉንም በግድም በውድም የኢትዮጵያን ወረራ እንዲካፈሉም እንዲደግፉም አድርጓቸዋል ። ባላባቶቹ የተለመደውን ካገር ላይ የሚወጣውን ግብር ለራሳቸው መውሰድ ሲያምራቸው እርሱ አብዛኛው ሀብት ለጦርነቱ ጉዳይ ይዋል ባይ ነው ።

የሆነ ሆኖ በዚህ ዓይነት ሱልጣን ኡመር ዲንና ይማም አህመድ እርስ በርሳቸው በመቻቻል በሼኮች ሽምግልና ገላጋይነት «ቅዱስ ጦርነት» ተብሎ ረዳት በሌለው በክርስቲያናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የታወጀውን የጦርነት ዓላማ በግድም በውድም በኅብረት እስከ ፍጻሜ አድርሰዋል (1) ።

ምዕራፍ ፵፫

የግራኝ አህመድ ወደባሌ መመለስ - የቃግማ [illegible]ት - የጆግናው የተክለ ሃይማኖት ፍጻሜ - በባሌ ግራኝ አህመድና ሸንቁር እንደተዋጉ (፲፭፻፳፱ ዓ.ም.) ።

ሱልጣን ኡመር ዲንና ግራኝ አህመድ የገሥሩት ጦብ እየባሰበት ቢሄድና ወደ ውጊያ ቢደረሱ ኖሮ ከወዲህ ለክርስቲያኖቹ የተመቸ ጊዜ ሊፈጠር በቻለ ነበር ። ወይም ሁለቱ ተዋግተው ሱልጣን ኡመር ዲን ቢያሸንፍ ኖሮ ሱልጣኑና ዓፄ ልብነ ድንግል ዕረፍት ያገኙ ነበር ። ነገር ግን ባለፈው እንዳነበብነው በኤሚር ሁሴን ቤን አቡበከር ጠንካራ መንፈስ የተነሣ እንደዚሁም በሼኮቹ አስታራቂነት ጠቡ ወደ ሰላም ስለተለወጠና በዚህ ዓይነት የእስላሞቹ ጕራ ስለጸና ለግራኝ አህመድ ያንኑ የዠመረውን የወረራ ሥራ ለመቀጠል ምንም የሚያውከው ነገር አልተገኘም ። ባጠገቡ ካሉት ከቱርኮችና ከዓረብ ተዋጊዎች ጋር በወገኖቹ በኩል ሱልጣኑ የበላይ - ታዛገፉ ሲሆን በወዲህ ደግሞ ባለፈው በንጉሡ ነገሥቱ ላይ በሽምብራ ኰሬ ያገኘው ድል ሁሉም ተደማምሮ የወደፊቱን ጦርነት ለመቀጠልና የመላዋ ኢትዮጵያ ጌታ ለመሆን ሙሉ ልብንና ድፍረትን ሰጠው ።

ከኡመር ዲን ከታረቁ በኋላ ግራኝ አህመድ ለሱልጣኑ ወዳጅነቱን በይፋ ለማሳየት ወይም ለመካስ ሲል ባለፈው እንደተገነዘብነው የመሬሃን ባላባት ሂራብ የሱልጣኑን አሽከር ገድሎ በሸፈተ ጊዜ እርሱን ለመውጋት ግራኝ አህመድ ከሱልጣኑ ጋር አብሮ ሄደ ። ይኸም ከፖለቲካውና ከስተዳደሩ ዘዶ ጋር የተያያዘ ጉዳይ መሆን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 286. 295. 326. 339. 395

አለበት ። በዚህ ዓይነት ሡልጣኑን በተቻለ መጠን በማስደሰት ያለፈ ቂሙን አስረ ሱቶ በርሱ እስከመጨረሻ ሊጠቀምበት እንደፈለገ ያሳያል ።

መሬሃን የተባለው የሱማሌ ሕዝብ ከኡጋዴን ምዕራብ - ደቡብ ከመጁርቲኗ ምሥራቅ ከዶሎ ባሐንቱ ሰሜን የሚገኝ ሕዝብ ነው ። ባላባቱ ሂራቡ አባቱ ጉይታ ቴድሩሩ (ጌታ ቴዎድሮስ) እያቱ አዳም ይባላል (1) ።

የስሙ ዓይነት ጉይታ ቴዎድሮስ ሲባል የትግሬና የአማራ ዘር ያስመስለዋል። ምናልባት በሰሜን ኢትዮጵያ በለው (ብሌን) ከሚባለው ነገድ ተነጥለው ከትግሬ ወደ አዳል አገር ከተዛወሩት ውስጥ ይሆናል ። ዓረብ ፋቂህ የበለው ሕዝቦች አባታ ቸው በኤሚር ሰዓዲን ዘመን (፲፩ኛው መቶ ዓ. ም.) ከትግሬ ወደ አዳል እንደመ ጣና ሰዓዲን ልጁን ድሮለት እንደነበረ ፤ ስሙም አብደላ እንደተባለ የርሱም ተወ ላጅ ወንድ ሲሆን ኡርአይ (አውራይ) ሴት ስትሆን በዓትያ ይባሉ እንደነበሩ ይገል ጻል (2) ።

በዚሁ ምክንያት የግራኝ ሚስት ድል ወንበራ በተጨማሪ በዓትያ ወይም ባቲያ ትባላለችና የእርሷም ዘር ከነዚሁ ከትግሬ ክርስቲያኖቹ ጋር ባለመስማ ማት ተለይተው ወደ አዳል ከተዛወሩት ከበለው ወገን መሆኗ ነው ። የሂራቡም አባት ጉይታ ቴዎድሮስ እንደነአውራይ ኡስማን ፤ እንደነ አውራይ አቡን ፤ ከዚሁ ከበለው (ብሌን) ዘር ሳይሆን አይቀርም ። ይሁን እንጂ ሂራቡ ከግራኝ ጋር መጥቶ ክርስቲያኖቹን ለመውጋት በመዝመሪያው ላይ ያልተስማማበት ምክንያት ምንም በሃይማኖት ብንለያይ በዘር አንድ ነንና አማሮቹንና ትግሬዎቹን መውጋት ቅር ብሎት ይሆን ? ። በኋላም ግዴታ ሲሆንበት ራሱ ሳይመጣ በልጁ አዝማችነት ጦሩን ሰጥቶ ከግራኝ ጋር ሆኖ እንዲዋጋ መላኩ በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ተጠቅሷል (3) ። ነገር ግን ወደፊት እንደምናነበው አቡበከር ቀጭኑ ደብረ ሊባኖስን ላለማቃ ጠል ዕርቅ ሲያራደር ተደብቆ ሄዶ ያቃጠለው አንድ የበለው ተወላጅ ነው ።

ራሱ ሳይሄድ በልጁ አዝማችነት ጦር መላኩ ባንድ ወገን ባገራችን ተቀምጦ ያገራችንን ሀብት እየበላ እስላም ነኝ እያለ ከኛ የማይተባበር ከሐዲ ነው የሚል ስሜት እንዳይፈጥርበት ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ከሡልጣን ኡመር ጋር ስምምነት ስላ ልነበራቸው የሡልጣኑን አሽከር ኖኅብ ላይ ስለገደለበት ሡልጣኑ ሊወጋው ሲሄድ ከእርታቸው በኋላ ግራኝ አህመድም አብሮ ሊወጋው ሄደ ። ሂራቡም ሡልጣኑና ይማሙ ባንድነት ስለመጡበት ለመመለስ እንደማይችል ተገንዝቦ ያለውን ሀብ ትና ከብት ሰጥቶ ታርቆ ገባ ።

የሂራቡ ጠብ በዚህ ዓይነት ካለቀ በኋላ ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን ለመው ረር ያቀደውን አሳብ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ወደ ሐረር በመመለስ ፊንታ ከመሬሃን ወደባሌ በቀጥታ ከሡልጣኑ ጋር ለመምጣት ቢጠይቀው ሡልጣኑ ሰዌ ያከሚልና

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 35 - 36 የሬኔ ባሴት ማመልከቻ ቍጥር 1
(2) ” ” ገጽ 10 - 11
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 34

ISIC

አንተ ሂደህ ተዋጋ እኔ ግን ወደ ሐረር እመለሳለሁ ብሎት ሲሄድ የልግም ነገር እን ዳለበት ያመለክታል ።

የሱልጣኑ ከግራኝ ጋር ኢትዮጵያን ሊወጋ አለመምጣት ብዙ ትርጉም ሊኖ ረው ይችላል ። ምናልባት የነቢዩን መሐመድ አጐትና ስደተኞች ያስተናገዱትን ፥ በዚሁ በነቢዩ የተመሰገኑትንና አትንኩዋቸው የተባለውን ነቢያዊ ትእዛዝ ለማክበ ርና ጨርሶ ኢትዮጵያን ለመውረርና ለማጥፋት ግራኝ ባቀደው ዓላማ አለመስማ ማት ይሆን ? ወይስ ገና ጠባቸው ሳይረሳና በሙሉ ሳይደመሰስ በድል አድራጊው ይማም አህመድ ገናንነት መካከል መዝመቱ ምንም የኩራት ስሜት ስላልሰጠው ይሆን ? ወይም ሱልጣናዊ መስፍንነቱ በእርሱ እጅ መሆኑ እየተሰማው ዳሩ ግን ለስሙ የበታቹ የሆነው ይማም አህመድ ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ግንባር ባገኘው የተ ደጋገመ ድል ያገኘው ዝና የርሱን ስምና ሥልጣን ሸፍኖበት በዚሁ ምንም ቢታ ረቁ ውስጠ ንዴት ይኖረው ይሆናል ።

ስለዚህ ሂራቡን አሳምነው ካስገቡ በኋላ ሱልጣኑ ወደ ከተማው ወደ ሐረር ሲያቀና ግራኝም በቅርቡ ጊዜ የታረቀውን ሱልጣን አብረን እንሂድ ብሎ ለማስገ ደድ ስለአልፈለገ ወይም ስለአልቻለ ራሱ ወደ ባሌ ጦርነቱን ለመቀጠል መጣ ። ከባሌም ቃግማ ወደ ሚባለው አገር መጥቶ አቡበከርን ከጦር ጋር ልኮ አዝማች ተክለ ሃይማኖትን ከነሕይወቱ አስማረከና ምርኮኛውን እንደ ገጸ በረከት ለአደን ሱልጣን ልኮ ሚስቱን የራሱ ዕቁባት አደረጋት ። ተክለ ሃይማኖት ቀድሞ እስላም ሆኖ ከግራኝ ጋር የነበረ በኋላ ግን ከግራኝ ወደ ፃ፭፴ልብነ ድንግል ዞሮ የቃግማን ግዛት ተሾሞ በክብር የተቀመጠና እስላሞቹንም ብዙ ጊዜ እየወጋ ያስቸግር የነበረ ስለሆነ ግራኝ ከነሕይወቱ እንዲማርከው ለታወቀው የጦር አለቃው ለኤሚር አቡ በከር ቀጢን በጥብቅ አደራ እንዳለው ከዝርዝር ታሪኩ ጋር ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ ሁኔታውን እንመልከት ።

«. . . . . ወደ ባሌ ጉዟቸውን ቀጥለው ዋቢ ወንዝ ደረሱ . . . . . ። ከ፫ ቀን በኋላ ሚዛ እሚባል ሥፍራ ደረሱና ሠፈር ሆኑ ። በዚህ ሳለ ይማም ወታደሩን እሁ ለት ከፈለው ። አንዱን ክፍል ለአውራይ አቡን ሰጠና አዳል ገለት ላይ እንገናኝ ብሎ ላከው ። አውራይ በሰረገዳ በኩል አድርጎ ወደ ቃግማ (ቃጅማ ?) ሄደ ። አንደ ኛው በአቅራ በኩል ወደ ባሌ ሄደ ። ይማም ግን በባሌ መንገድ ጉዞውን ዠምሮ ሲጓዝ ወደ እስላም አገር ወርደው ለመስለም የሚፈልጉ የባሌ ክርስቲያኖች በመን ገድ አገኘና የወዴት አገር ሰዎች ናችሁ ? ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም የባሌ ሰዎች ነን አሁን እንደናንተ እስላም ለመሆን ወደ ጃ (ጋ) ልብ እንሄዳለን አሉት . . . . . . ስለኛ ምን ትሰማላችሁ ቢላቸው ምንም አልሰማንም ። ስለናንተ የሚናገርና የሚያ ወራ ባገር ውስጥ የለም አሉት ። አገሩስ እንደምንድነው ? አገሩን የሚያስተዳድ ረው ሹምስ ማን ይባላል ? ብሎ ቢጠይቃቸው ያገሩ ገዥ የንጉሡ እማች አዝማች ደገልሃን ይባላል ። አሁን ወታደር ይዞ ባገሩ ላይ ያለው የርሱ ሹም ሸንቁር የሚባ ለው ነው ፤ ብለው መለሱ ። የሚቀመጥበትንም ሥፍራ ቢጠይቃቸው ሸንቁር በዛ ላህ ፤ ተክለ ሃይማኖት በቃግማ ይገኛሉ ብለው መለሱለት ።

ተክለ ሃይማኖት እስላም ነበር ። ገራድ አቡን ወዚር የነበረ ጊዜ ጋሻ ጃግሬው ነበር ። ጌታው ከሞተ ወዲህ ከይማም ጋር ሆኖ አገር ግዛትም አግኝቶ ነበር ። በኋላ ግን አገር በድሎ ይማም ቢሸረው ወደ ሀበሻ ንጉሥ ዘንድ ገብቶ የቃግማ ገራድ ተብሎ በሹመት የነበረ ነው ።

ይማም ተክለ ሃይማኖት በላይኛው ወይስ በታችኛው ቃግማ ነው የሚገኘው ? ብሎ እነዚህኑ ሰዎች ቢጠይቃቸው በፊት ከላይኛው ነበር ፣ አሁን ግን ወደታችኛው ወርዷል ብለው መለሱለት ። ልትመሩኝ ትችላላችሁን ቢላቸው ደስ ይለናል አሉት ። አሁን ከዚህ ስንነሣ እርሱ ዘንድ በምን ጊዜ እንደርሳለን ቢላቸው ሊነጋጋ ሲል እንደርሳለን አሉት ።

ስለዚህ እዚሁ እሥፍራህ ቆይ ለማለት ወደ አውራይ አቡን ላከና እርሱ የታወቁትን ጉበዛዝት እነድል ሰገድን እነዘሀርቡይ ዓሊን ፣ እንደፋራታሃም ሳቱን ፣ እነገራድ አህሙሹን ፣ እነቀጢን አቡበከርን . . . . . በጠቅላላው ፴ የሚሆኑ ፈረሰኞች መረጠና የሚዋጋበትን ባንዲራ ጨምሮ ለአቡበከር ቀጢን ሰጠው ። እነዚያንም ሁለት ክርስቲያኖች እንዳይሸሹ አሣሥረና ይኸን ጦር እተክለ ሃይማኖት ድረስ አድርሱ ፣ ይኸን ያደረጋችሁ እንደሆነ ደስ የሚያሰኛችሁን ነገር እናደርግላችኋለን አላቸውና እነሱም እሺ አሉ ። ወደ ቀጢን አቡበከር ዘወር ብሎ "ተክለ ሃይማኖትን ይዘህ ያላመጣህልኝ እንደሆነ ከደንበኛ ተዋጊ አልቆጥርህም በመካከላችሁ በክርስቲያኖች ያልተበደለ ማን ይገኛል" ሲል ሁሉም "እውነት ነው" እያሉ ጮሁ ።

ISIC

. . . . . . ከእኩለ ቀንም በኋላ እነዚህ ወደ ተክለ ሃይማኖት ሲጓዙ ይማም . . . . . . አቅራ ወደሚባል አገር ደርሶ ከዚያም የክርስቲያኑን አገር እየዘረፈ ወደ አዳል ጃላት በደጋው ክፍል ወደ ቃግማ ዘመተ ። አቡበክር ቀጢን ግን እነዚያን ሁለቱን መሪዎቹን እንደታሠሩ እፊት አስቀድሞ ሌሊቱን ሙሉ ሲጓዝ አድሮ ሊነጋ ሲል መሪዎቹ ቆም ብለው ሲመለከቱ፡ በኋላችሁ ምን ይታያችኋል ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም ተክለ ሃይማኖት ያለበት ሥፍራ ከነእሳቱ ይታየናል አሉ ። በዚህ ጊዜ ኤሚሩና ጓደኞቹ ምክር ይዘው ገሚሶቹ ከበን እንውጋው አሉ ። አቡበክር ቀጢን ግን አገዛማች ተክለ ሃይማኖትን እጇን ይገር ለይማም ለማቅረብ ተስፋ ስጥቻለሁ ። ከበን የወጋነው እንደሆነ በጭለማ ሲያመልጠን ይችላልና እስኪነጋ ብንቆይ ይሻላል ፣ ብሎ መለሰ የቀሩትም አንተ አለቃችን ነህና የሚመስልህንና የተሻለውን አድርግ ብለውት በዚሁ ተስማምተው ከበቅሏቸው ወርደው እመሬት ተቀመጡ ፣ ኤሚሩም እንግዲህ የያሲንን ሱራት ድገሙ አላቸው (1) ።

(1) በኛ ዘንድ ለመጽደቅ ልፋፈ ጽድቅን ድገም ወይም አብረሀ ተቀበር ፣ የጠፋን ከብት እውሬ እንዳይበላው ከዳዊት መዝሙር ዘየኀድርን ድገም እንደሚባለው እስላሞቹም ለመሐመድ ከሰማይ ገብርኤል አምጥቶ ሰጠው ብለው በሚያምኑት ቁራን ውስጥ ያለውን 114 ምዕራፍ እያንዳንዱን ላንዳንድ ጉዳይ መድበውታል ይኸም ያሲን የሚባለው 36ኛው ምዕራፍ ሰው ታሞ ሲያጣጥር ወይም ጭንቅ ሲያዘው የሚደገም ነው BLACHERE ትርጉም ገጽ 468 ተመልከት ። ቃሉን በአማርኛ ለማንበብ የፈለገ እነሰይድ መሐመድ ሴዲቅ የተረጐሙትን ምዕ.36 ክፍል 22 ገጽ 309 - 313 መመልከት ይበቃል ።

ይኽ ሁሉ ሲሆን ተክለ ሃይማኖት የሌሊቱን ጊዜ በመጠጥ አሳልፎ ነበር ፡፡.... በዚህ ጊዜ ይማም በዘመተበት በኩል የእሳት ቃጠሎ አየና ይህ የማየው እሳት ምን ድነው ? ብሎ አጠገቡ ያሉትን ቢጠይቅ ሌባ ወይም ተላላፊ ሽፍታ ቤት አቃጥሎ ይሆናል ሲሉ መለሱለት ፡፡ እርሱ ግን አይመስለኝም የጠላት ያንድ ክፍል ወታደር ነው ፤ ፈረሶቻችሁን ጫኑ ሂደን እንዋጋለን ብሎ አዘዘ ፡፡ አቡበከር አጠገቡ መሆኑን አያውቅም ነበር . . . . . ከዚህ በኋላ አቡበከር ቀጢን ከታሠሩት ሁለት ሰዎች አንዱን አሥሮ አስቀርቶ ሁለተኛውን ከሦስት እስላሞች ጋር ሆኖ እተክለ ሃይማኖት ሠፈር ድረስ ሂደው ሰልለው እንዲመለሱ «እተክለ ሃይማኖት ሠፈር ሂዱና ተኝቶ እንደሆነ ወይም ምን እንደሚያደርግ መርምራችሁ ተመለሱ ፡፡ ጓደኛህ እኛ ዘንድ ይቀራል የከዳኸን እንደሆነ እርሱን እዚህ ገድለን እንዋጋለን ድልም እናደርጋለን» ብሎ ላካቸው ፡፡ እነሱም በድብቅ እተክለ ሃይማኖት ሠፈር ድረስ ሂደው ፈረሶቹ መጫናቸውን ተመልክተው ተመለሱና ለአቡበከር ነገሩት ፡፡ በዚያን ጊዜ እስላሞቹ ፋቲሀህ (ጸሎት) እየደገሙ ድልን ለማግኘት ጸለዩ (1) ከዚያ ሲነጋ አቡበከር ቀጢን ሞባረቅ (መብረቅ) እሚባለው ፈረሱ ላይ ወጣ ጥሩሩን ለብሶ ረዥም ጦሩንም ያዘ ፡፡የቀሩትም ሁሉ እንደዚሁ አደረጉና ጦራቸውን እሾለው የፈረሶቻቸውን ልባብ (ልጓም) ለቀው . . . . . ወደ ጠላቶቻቸው ሠፈር ገቡ ፡፡ ተክለ ሃይማኖትም እነሱን ሲያይ እፈረሱ ላይ ወጣና ወታደሩ አጥሩ ውስጥ እንደነበረ እርሱ አበራፍ ሆኖ አቡበከር ጦር ፡ እርሱ ሰይፍ ፡ እንደያዘ መመታታት ጀመሩ ነገር ግን አቡበከር ከውጭ ፤ ተክለ ሃይማኖት ከ[illegible]ም ስለነበሩ አልተጐዳዱም ፡፡

እስላሞቹም ገብተው ለመዋጋት በሩ አንድ ብቻ ሆኖባቸው ተቸግረው ሳለ ድል ሰገድ የተባለው ፈረሰኛ ከንሮ ዞሮ አጥሩን በፈረሱ ጥሶ "የሲም ፈረሰኛ" እያለ ፎክሮ ገብቶ ጦርነቱን ሲጀምር ጓደኞቹ ተከትለው ገቡና የሁለቱም ወገን ወታደር ተደባልቆ ይዋጋ ጀመር ፡፡ ተክለ ሃይማኖትና አቡበከርም እንደዚያው እን ደጀመሩ ሲዋጉ ክርስቲያኖቹ ሽሽት ጀመሩ ፡፡ ተክለ ሃይማኖትም ወደነርሱ ዞሮ ወዴት ነው የምትሸሹት እያለ ሲቆጣ አቡበከር ወደ ውስጥ ለመግባት ቻለ ተክለ ሃይማኖትም እንደገና ተመልሶ ገጠመው ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ የክርስቲያን ፈረሰኛ ለጌታው ረድቶ አቡበከርን ሊመታው ሲል ዘሀርቡይ ክርስቲያኑን መታና ከፈረሱ ላይ ጣለው . . . . . ፡፡ አቡበከርም ተክለ ሃይማኖትን ወግቶ ከኮርቻው ላይ ገለበጠውና ማረከው . . . . . . ፡፡ ጌታቸውም ሲማረክ የተረፉት ክርስቲያኖች ሸሹ ፡፡ የቀሩትም ሞቱ ፡፡ በዚያ የነበሩት ወዲያና ወዲህ ሳይሉ ባጥር ውስጥ እንዳሉ ተገኝተው ተወሰዱ ፡፡

(1) ይኸም ጸሎት በቁራን ምዕራፍ ፩ በ፯ አንቀጽ የተከፈለ እንደ መቅድም አል ፋቲሐህ (የመክፈቻ ምዕራፍ) ሆኖ በስመ እግዚአብሔር መሐሪ ወይም በስመ አብ ተብሎ እግዚአብሔርን በቋንቋቸው "አል ሀምዱ ሊላሂ" ብለው የሚያመሰግኑበትና ቀናይቱን መንገድ ምራን ብለው የሚለምኑበት ነው ፡፡ ቁራን BLANCHERE ወደ ፈረንሳዊ የተረጐመውን ገጽ 29 እንደዚሁም የነሰይድ መሐመድ ትርጉም በአማርኛ ምዕ. ፩ ክፍል 1 ገጽ 1 - 2 ተመልከት ፡፡

አቡበክር ተክለ ሃይማኖትንና ሚስቱን ወስዶ እይማም ፊት አቀረባቸው ።
ይማም ተክለ ሃይማኖትን እንደ ገጸ በረከት ለአይን ሱልጣን ላከለትና ሚስቱን
ለራሱ ዕቁባት አደረጋት ። ስሟም ሃጂራ ተብሎ ተሰየመ (1) ። እርሷም የሀበሻን
አገር ድል በመታበት ጊዜ ሁሉ ትከተለው ነበር ። ከዚህ በኋላ እስላሞች ወደ ዋባ
ናት ሄዱ ። በዚያም ይማም አህመድ ዘሀርቡይ መሐመድ ለሚባለው ለአጎቱ ልጅ
፩፻ ፈረሰኛ ብዙ የእግረኛ ጦር ባንዲራ ጨምሮ ሰጠውና ወደ ባሌ መኸል ወደ
መሎዋ (መሉአ ማሎ) እንዲዘምት ላከው ። እርሱም በየመንገዱ ያገኘውን እየዘ
ረፈ እያቃጠለ ወደፊት ሲሄድ የክርስቲያን ፈረሰኞች እየጋለቡ ሲመጡ አሊጋራህ
የዘርባው የሚባል ፈጣን ፈረሰኛ የራሱን ፈረስ ልጓም ለቆ ወደነሱ ሽምጥ ሲጋልብ
ኲርቻው ተበጥሶ ወደቀበት ። እሱም እንደ፦ነይለኛ ነፋስ ተወርውሮ ወደቀና አንድ
ፈረስ ልቡን ረግጦ ገደለው . . . . . .። በባሌ ሻንኩር (ሽንቁር) የሚባል የራስ ደገ
ልሃን እንደራሴ ነበር ። እርሱም በተክለ ሃይማኖት ላይ የደረሰውን የባሌንም መዘ
ረፍ ስለሰማ ወታደሩን አሰልፎ ወደ ይማም ጉዞ ዠመረ ። በተጠጋም ጊዜ ለስለላ
የላካቸው ፯ ፈረሰኞች ፈረስ ይዘው ባንድ ቦታ የተቀመጡትን እስላሞች አግኝተው
ገደሏቸው ። እስላሞቹ ግን ተጨዋጨኸው (ወገኖቻቸው እንዲሰሙ) ነበርና
ይማም ይኸን ሲሰማ እፈረሱ ላይ ወጥቶ ሲጋልብ የቀሩት ተከተሉት ። ነገር ግን
ጠላቶቻቸውን አላገኙም . . . . . . በባሌ የሚገኙ ዓረቦችና ሸሪፎች መጥተው ከይ
ማም ተገናኙ ። እርሱም በደህና ተቀብሎ የሽልማት ልብስ አለበሳቸው . . . . . .።
ከዚያ አቡበክር ወደ ዋቢ ሄዶ አውራይ አህመድ . . . . . እፊት ሲገባ ከኋላ ይማም
ተከትሎት ነበር ሽንቁር ጦሩን እ፫ት ላይ ከፍሎ አንዱን እፊት ፪ኛውን ከማኸል
፫ኛውን ደጀን አድርጎ እንዲዋጋ አሰልፎት ነበር ። የመዠመሪያውም ጦር እፊት
ቀድሞ ከአውራይ አህመድ ዲን ጋር ተገናኝቶ ትልቅ ውጊያ ተዠመረ ። ክርስቲያ
ኖች ብዙ ስለነበሩ እስላሞቹ ወደኋላ አፈገፈጉ ፤ አህመድ ዲን ግን ገትሮ ሲዋጋ በ፲
ጦር (፲ ጊዜ ?) ተወግቶ ቆስሎ ከሞት ተረፈ ።

ይማም ከኋላ ሆኖ የነዚህን መዳከም ሲያይ ገሥግሦ ደረሰላቸው . . . . .። ክር
ስቲያኖቹም የርሱን ጦር መምጣት ሲያዩ ሸሹ . . . . . .። ቢሆንም በዚያ ዙሪያ ብዙ
ጦርነት ሆነ . . . . . . ይማም ለጓደኞቹ እንደዚህ አላቸው ። እዚህ በባሌ ያለንበት
ቦታ አደገኛ ነው ። የባሌም ሕዝብ ሰይጣን ነው ፤ የባሌን ሰዎች የጦርነት መላ የሚ
ያውቅ ማነው ብሎ ጠየቀ ። አጠገቡ ያሉትም ገራድ ካሚል ነው ብለው መለሱ
ለት ። ገራድ ካሚልም እኅቱን ሙኒሣህን ያገባ የይማም አማች ነው ፤ እርሱም
የባሌ ሕዝብ እያለፈ አደጋ በመጣል እንጂ ፊት ለፊት ተሰልፎ አይዋጋም ። ተሰል
ፈህ ብትገባ ከኋላ ያለውን አደጋ ጥለው ይወጋሉ ። ፊት ለፊት ብትገጥማቸው ሩቅ
ሳይሄዱ ይሸሻሉ ይህ ነው የባሌ ጦርና ሕዝብ የጦርነት አሳብና መላ ሲል ለይማም
አስረዳው ። ይማም ግድ የለም እኛም ተንኮል ሠርተን እናታልላቸዋለን አለና ለኤ
ሚር አቡበከር ፤ ኤሚር ሙጋሂድን ፤ አብሳማ ኑርን ፤ ገማልዲንን ፫ ፈረሰኛ ጦር

(1) ሐጂራህ ማለት ስደት ማለት ስለሆነ የስደት ሚስቱ እንደማለት ይሆን ? ያውም እርሱ አሳደደ
እንጂ አልተሰደደም ።

ISIC

ሰጠውና አፊት አፊት እየሄዳችሁ እፊታችሁ ካገኛችሁት ጋር ብቻ ተዋጉ ተመልሳችሁ እኛን ለመርዳት አታስቡ እኛም እናንተን እንረዳም ብሎ እነርሱን አስቀድሞ ላከና እርሱ የቀረውን ጦር ከብትና ንዝ ይዞ ከኋላ ይጓዝ ዠመር ። ከዚህ በኋላ የክርስቲያኖች ጦር ድንገት . . . . . ደረሰና አራት ላይ ተከፍሎ ሁለት የጦር አለቆች ወደነ አቡበከር ሄዱና ገጠሙ ። አንድ ሰዓት ውጊያው እንደቆየ የክርስቲያኖቹ አዝማች ሰሎሞን በአህመድ ዲን እጅ ተመትቶ ሞተ ። ሊላው ሹም ደግሞ በአቡበከር እጅ ሲሞት ክርስቲያኖቹ ሸሹ ።

ይማም ባለበት በኩል . . . . . ሲሙ (ሰምዖን) የሚባል የጦር አለቃ የሚመራው ጦር . . . . . ከይማም ጋር ተጋጠመ . . . . . ይማም አህመድ ሲዋጉ የመጡትን ክርስቲያኖች ባየ ጊዜ . . . . . . ጦሩን አሰለፈ ። የመሬሃን ፤ የጎርጎራ የኤል ሐውያህ የቀስት ጦረኞች ፡ በሺ የሚቆጠሩ እንደዚሁም ኰሽም ኑር ፡ ገራድ ናስር ፡ ድል ሰገድ . . . . . ያሉበት ፴ ፈረሰኞች ነበሩት ። ጦርነቱን የዠመረው ድል ሰገድ ነው ። እርሱም አሥራት ከሚባለው የጦር አለቃ ጋር ብቻ ለብቻ ገጥመው ሲዋጉ ድል ሰገድ አሥራትን ከፈረስ ላይ ገልብጦ ሲጥለው ናስር የሚባለው በሰይፍ መትቶ ጭንቅላቱን ከአካሉ ለይቶ ገደለው ። የቀሩትም ክርስቲያኖች ሸሹ ። ይማም አህመድ በበኩሉ ከብት ሊማርኩ ከነበሩት የክርስቲያን የጦር ሠራዊት ጋር ተጋጥሞ ሲዋጋ ከርሱም ጋር እነፋራቃሃም ሁሴን እነኤሚር መሐመድ ዘሀርብይ . . . . . . እየተጯጯሁ የእግዚአብሔርን ስም እያነሱ ተዋግተው አሸነፉ ።

ISIC

ከዚህ በኋላ በየግንባራቸው ክርስቲያኖችን ያሸነፉት እስላሞች ድልባድ ከሚባል ሥፍራ ላይ ተሰብስበው በዚህ ቀን ድል እንኳን ደስ ያለን ሲባባሉ . . . . . ቆይተው ከዚያ ምርኮአቸውን ሰብስበው በጅዳህ በኖጎብ በኩል አድርገው ሁሉም በየአገራቸው ተመለሱ ። ይማም አህመድም በድል አድራጊነት በደስታ ሐረር ገብቶ ሁለት ወር ተቀመጠ ። የማረከውንም ምርኮ ለየጓደኞቹ አከፋፈለ» ሲል ዓረብ ፋቂህ የባሌን ጦርነት እዚህ ላይ ያቆማል (1) ።

በዚህ ምዕራፍ ግራኝ አህመድ ከሐረር ወደ ባሌ ዘምቶ የፈጸመውን ወረራ በዝርዝር እንመለከታለን ። ራስ ደገልሃን ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱን ተከትሎ ወደ ቤተ አምሐራ (ወሎ) ስለሄደ ባሁን ጊዜ (፲፰፻፳፪ ዓ. ም.) የባሌን ጦር የሚያዘውና አገሩን የሚያስተዳድረው እንደራሴው ሽንቁር ነው ማለት ነው ። የባሌም ሕዝብ እንደዛሬው አብዛኛው በእስላምና በክርስቲያን የተከፋፈለ ሲሆን በነዚህም መካከል በሁለቱም እምነት ያልተያዘ አረመኔ ወይም የስም እስላም አለዚያም ለስሙ ብቻ ጥምቀተ ክርስትናን ተቀብለው ከአረመኔነት ምንም ያህል ያልራቁ የስም ክርስቲያን ይኖሩበት ይሆናል ።

ባለፉት ዓመታት የነደገልሃንን ፤ የነራስ ነቢያትን ፤ የንጉሠ ነገሥቱን መሸነፍና የግራኝን ማሸነፍ የተረዱት የስም ክርስቲኖች ከአዲሱ ገዥ ከግራኝ አህመድ ጋር ሃይማኖታቸውን ለማገናዘብና ኑሮአቸውን ለማስማማት እስላም ለመሆን ከባሌ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 147 - 170

(ወደ ጀልብ ?) ሲሄዱ በመንገድ ላይ ከግራኝ ጦር ተገናኙ ። ሁል ጊዜ ግራኝ በሰላይ አጥብቆ መጠቀምን ስለሚያውቅበት በነዚህ ሰዎች ጠቋሚነት ሸንቁርና ይልቁንም ከርሱ ከድቶ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የገባውን የቃግማውን ገኘር ተክለ ሃይማኖትን ከነሕይወቱ ለማስማረክ በነዚህ ሊሰልሙ በሚጓዙ ሰዎች እንደተጠቀመባቸው ተመልክተናል ።

ላገሩ የቀረውም ቢቀር ለቀበሌው እንግዳ የሆነው አቡበክር ቀጢን እነዚህን ሰላዮች እንዳያመልጡት አሥሮ በነርሱ መሪነት ሌሊቱን ወደ አለበት ሠፈር ሲጠጋ ፡ ጊዜውም የጦርነት ሰዓት መሆኑን እያወቀ ተክለ ሃይማኖት በራሱ ግዛት በሩቁ ነቅተው የሚጠባበቁ ሰላዮና ቃፊሮች አለማስቀመጡ በሚዋጋበት ጊዜ ወይም ከተማረከ በኋላ ሳይጸጽተው አይቀርም ። ዳሩ ግን ዋጋ የሌለው ጸጸት ነው ። ይሁን እንጂ ከመማረኩ በፊት በእንዴት ያለ ጀግንነት የተዋጋ በመሆኑ ሊመሰገን ይገባዋል ።

ግራኝ ተክለ ሃይማኖትን እንደተመኘው ከነሕይወቱ ካገኘው በኋላ ባለፈው ቂሙ በመግደል ፈንታ የጦር መሣሪያና ተዋጊ ወታደር ከማይ ከሚያቀብሉት የዓረብ ባለሥልጣኖች ላንደኛው ለአደን ሱልጣን እንደ ገጸ በረከት አድርጎ ላከው ። ሙሴ ረኔ ባሴት የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከተረጐሙበት ከገጽ ፻፵፱ ላይ በዚህ ጊዜ የአደን ሱልጣን የነበረው ኤሚር (ወይም ኡመር) ቢን ዳውድ የሚባለው እ. እ. ቀ. ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. በቱርኩ ISIC በሶሌይማን የተገደለው ሳይሆን አይቀርም ብለዋል ፡

የሆነ ሆኖ ግራኝ ጀግናውን ተክለ ሃይማኖትን ወደ አደን ከላከ በኋላ ሚስቱን ለራሱ ዕቁባት አድርጎ አቆይቶ በኋላም አገባት ከርሷም ልጅ ወልዷል ። ይቺን ሴት ለራሱ ሚስት ማድረጉ ሴትዮዋ ዓይበስ ለሐዬ በሚባለው ትልቅ ሰው በኩል ካዬ ልብነ ድንግል የቅርብ ዝምድና ስላላት በርሷ አማካይነት ብዙ ወገን ለመሳብ አስቦ ይሆን ? ወይስ ቁንጅናዋ ማርኮት ይሆን በትክክል አይታወቅም (1) ። ወደፊት እንደምናገኘው ይቺን ሴት ግራኝ በብዙ የጦርነት ቦታና በጉዞ ላይ ስለማይለያት እንደ ድል ወንበሩ ያከበራትና የወደዳት ይመስላል ። ስሟንም ሐጂራሀ (የስደት ሚስቱ?) ብሎ ሰየማት ።

ዓረብ ፋቂህ በሸንቁር የጦር ግንባር በመዠመሪያ ክርስቲያኖቹ ድል አድርገው ማባረር ከዠመሩ በኋላ ግራኝ ይኸንኑ በሩቅ ተመልክቶ በግልቢያ ደርሶላቸው እስላሞቹ ማሸነፋቸውን በገለጸበት ቦታ የባሌ ሕዝብ እንደቀሩት ተዋጊዎች ባንድነት ተሰልፎ በማለቅ ፈንታ እንደዛሬው ዘመን የደፈጣ ጦርነት (ጐሪላ) ከፊትና ከኋላ አደጋ እየጣሉ ግራኝን እንዳስቸገሩትና «የባሌ ሕዝብ ሰይጣን ነው ምን ማድረግ ይሻላል» ብሎ የእጎቱን ባል ገራድ ካሚልን ከመጠየቅ እንደደረሰ የተንኮላቸውንና የአወጋጋቸውንም ዘዴ ከአማቹ ከሰማ በኋላ ለተንኰላቸው ተንኰል እንደ ፈጠረላቸው ተገንዝበናል ።

(1) ዓይበስ ለሐዬ በናቱ በኩል ካዬ ልብነ ድንግል ስለመዛመዱ ዓረብ ፋቂህ ገጽ 269

ዓረብ ፋቂህ አሥራት የሚባለው የጦር አለቃ ድል ሰገድ ከሚባለው የእስላም የጦር አለቃ ጋር አንድ ላንድ በሚዋጉበት ጊዜ ናስር የሚባለው በሰይፍ (ምናልባት ከኋላው ሆኖ) አንገቱን መትቶ ጭንቅላቱን ከአካሉ እንደለየው ፤ ሰሎሞን የሚባለ ውን አህመድ ዲን የሚባለው መትቶ እንደገደለው ሲገልጥ ስለዋናው አዝማች ስለ ሸንቁር ፍጻሜ አልጻፈም ። ምናልባት ጠሩ ድል መሆኑን ሲያውቅ ሸንቁር የበላዩ ራስ ደገልሃንና ንጉሠ ነገሥቱ ወዳሉበት ወዳማራው አገር ወይም ግራኝ ወዳልደረ ሰበት ተጉዞ ይሆናል ። ንጉሠ ነገሥቱም መዠመሪያ ወደ አማራ አገር ከተጓዙ በኋላ ወደፊት በምናነበው በዓይፈርስና በዛሬ ጦርነት ጊዜ ከአማራ አገር ተመል ሰው መጥተዋል ። ይኸም የአማራ አገር የምንለው ዛሬ በወሎ ስም የሚጠራው ያን ጊዜ ቤተ አምሐራ የሚባለው መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

ምዕራፍ ፵፬

የግዛት ስፋትና ያገዛዝ መላላት የፈጠረው የጦርነት ጠንቅ - ከዳተኞቹ ወናግ ዣንና ልጁ ሲሙ (ስምዖን) ።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ኃይላቸው በርትቶ በደቡብና በምሥራቅ እስከ ሕንድ ውቅ ያኖስ እስከ ቀይ ባሕር ድረስ ያለውን ሰፊ የአዳልና የሱማሌ ነዋሪ ግዛታቸውን በቀ ጥታ በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ከወዲህ ከንጉሠ ነገሥቱ የተጣላ የክርስቲያን የጦር አለቃ የባሰበት ሸፍቶ ጫካ ይገባል እንጂ የአዳሎቹና የሱማሌዎቹ ባላባቶች ወይም አብዛኛ ጊዜ ሁለቱን ነገድ አጣምሮ የሚገዛው የወላስማ ተወላጅ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝና ገባር በሆነበት አጫጭር ጊዜ ውስጥ ወደነርሱ ገብቶ በመንግሥቱ ላይ አምጦ ምንም ያህል ሊያስቸግር አይችልም ነበር ።

ነገር ግን ባንድ ወገን በኢትዮጵያ ሰሜን ፈላሾችና ሌሎችም ነገዶች እልፎ አልፎ እየሸፈቱ ማስቸገራቸው ስለማይቀር በሌላው ወገን መንግሥቱ ባስተዳደር በቴክኒክ በዘመናዊ ጥበብ በወታደራዊ ትጥቅና መሣሪያ ያለው ድር ጅት ደካማ በመሆኑ የነገዱ ቁጥር የበረከተውን የሱማሌና የአዳል ባላባቶች በው ስጡ አሳምኖ በሙሉ ለረዥም ዘመን የተቆጣጠረበት ጊዜ በልክ ነው ። አገሩ ሰፋፊ ሥፍራው አብዛኛው በረሃማ የተወላጁ ቋንቋ የተለየ ፤ ሃይማኖቱ እስላም ወይም አረመኔ ከመሆኑ የተነሣ እንደ ዓፄ ዓምደ ጽዮን የበረታው ንጉሠ ነገሥት አንድ ጊዜ ከነወታደሩ እስከ ጫፍ ዘልቆ የሸፈተውን ለማባረር የሚቻል ሲሆን ለመማረክ ወይም አሳምኖ ለማስገበር ካልሆነ በቀር በየአውራጃው ፤ በየወረዳው ታማኝ ሹማምንት ሾሞ በየአማካዩ ሥፍራ ነዋሪ ወታደር አስቀምጦ የሸፈቱት የውጭ እርዳታ የሚያገኙባቸውን የነዘይላን ወደቦች በደንብ ይዞ ሊቆጣጠር ባለመ ቻሉ በየአውራጃው ያው ባላባቱ ከነልጅ ልጁ እየተከታተለ አገሩን ሲያስተዳድር ይኸው ባላባት ጉልበት ሲሰማውና ከማዶ ከዓረብ አገር አይዞህ ባይ ሲገጥመው እየ

ISIC

ሽፈተ ሳይመቸው በሩቅ ላለው ንጉሠ ነገሥቱ እየገበረ እስከ አሁን እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ደርሷል ።

ከባሌ ጫፍ እስከ ባብ ኤል መንደብ ከአውሳ ከደንከል እስከ በርበራ ከበርበራ እስከ መቃዲሾ ፤ ከመቃዲሾ እስከ ኪስማዮ እስከ ኬንያ ጠረፍ ያለውን ሰፋፊ የአዳል ፤ የኢሳና የሱማሌ ነገድ ባንድነት አስተባብሮ ለመግዛት ከፍ ያለ የማይበገር ኃይል ያስፈልጋል ። የየነገዱን ብዛት ዓረብ ፋቂህ በአሁኑ ጊዜ ከግራኝ ጋር ተባብረው የመጡትን መሬሃን ሐርላህ ጊሪ መለሳይ ይበሪ ሐርቲ ጀራን ማዛር ሀብር መጋዲ እያለ በዝርዝር በባደቄና በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ምዕራፎች ላይ የጠራቸውን እናስታውሳለን ። አሁንም በግራኝ ውስጥ ሆነው ጦርነቱን መቀጠላቸውን ወደፊት በየምዕራፉ እናነባለን ።

«በአፍሪካ ምሥራቅ የመገናመሪያው እርምጃ» በሚል አርእስት ሪቻርድ ባርተን የሚባለው እንግሊዛዊ በጻፈው መጽሐፍ የሱማሌዎቹን ብቻ የነገድ ቍጥር በዋና መደብ ከሦስት ላይ የሚገኘውን በዝርዝር ደግሞ እስከ አሥራ ስምንት ቅርንጫፍ አድርሶታል ። ስማቸውንም ፡

፩ኛ. ሬር ገራድ (ንጉሣዊ ቤተሰብ)
፪ኛ. ሬር ፋቂህ
፫ኛ. ሬር አብዱላህ
፬ኛ. ሬር ቢሂዱር
፭ኛ. በሆጋይ ሳላባይ
፮ኛ. አዳን ያኩብ
፯ኛ. ገራድ ኡመር
፰ኛ. ገራድ ዩሱፍ
፱ኛ. ገራድ ሊባን
፲ ኛ. ኑህ ኡመር
፲፩ኛ. አደን ሳዒድ
፲፪ኛ. ሬር ሐጂ
፲፫ኛ. ዱባይስ
፲፬ኛ. ዋርላባህ
፲፭ኛ. ባያባርሃይ
፲፮ኛ. ሬር ያሲፍ
፲፯ኛ. ሂንዱዱብ
፲፰ኛ. ሬር ጋርዋይና (1) ።

ISIC

እነዚሁ ሁሉ በየአቅራቢያቸው በፈረንሳዊ ፡ በእንግሊዝ ፡ በኢጣልያ እጅ ከቆዩ በኋላ ባሁኑ ጊዜ ግማሾቹ በኢትዮጵያ የቀሩትም በሱማልያ ሬፑብሊክ ውስጥ የሚገኙ ናቸው ።

ያፄ ዓምደ ጽዮን በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው የጦርነት ታሪክ የኡመር ወላስማ ...... ልጁ ሰበርዲን (ሳብር አድ ዲን) ለውጊያ እስከትሏቸው የመጣውን የአዳልና የሱማሌ የየባላባቶቹን ስም በንጉሥነት ብቻ የሚጠሩትን ቍጥራቸውን እስከ ፲፭ አድርሶታል ። ሲዘረዝራቸውም የአዳል ንጉሥ የሞራ ንጉሥ የበከላ ንጉሥ .... የፈድሴ ንጉሥ .....የሐርላ ንጉሥ ...... የሆባት ንጉሥ ...... እያለ ይጠራቸዋል ። ዋናውን መሪ ነሰረዲንን አንዳንድ ጊዜ የአዳል ንጉሥ ሌላ ጊዜ ከሐዲው ንጉሥ ሰብረዲን ይለዋል (2) ።

(1) First Footsteps in east Africa - R Burton Page 331
(2) ንጉሠ አዳል ንጉሠ ዕልዋን ..... ዡል ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 279 - 280

ስለዚህ እንደዚህ የበረከተውን ነገድ መቆጣጠሩ ስላቃተ ከታላላቆቹ ነገሥ
ታት ከነዓፄ ዓምደ ጽዮን ከነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ወዲህ የመዠመሪያውን ሹመቱን
በይፋትና በአዳል ላይ ካፄ ይዙና አምላክ ያገኘው የኡመር ወላስማ ልጆች ኃይል
በየጊዜው እየተሰማቸው በንጉሠ ነገሥቱ ላይ መሸፈት ብቻ ሳይሆን በየአቅራቢያ
ቸው ያለውን የይፋትን ፣ የደዋሮን ፣ የባሌን ሕዝብ ክርስቲያኑን ማስለም ከንጉሠ
ነገሥቱ በሹመትና በሌላም የተቀየመና የሸፈተውን ተቀብለው እያስተናገዱ በማ
ስለም በሚገዙት ክፍል ያውራጃ ሹመት እየሰጡ ማስቀመጥ ከዠመሩ ቆይተዋል ።
ለምሳሌ ዓፄ ዓምደ ጽዮን በዘመኑ (፲፫፻፺፯ - ፲፫፻፴፯ ዓ. ም.) የሸፈተበ
ትን ሰበርዲንን ተዋግቶ ካሸነፈው በኋላ «በል ባንተ ውስጥ ክርስቶስን እየካዱ የሰ
ለሙትን ሰብስበህ አምጣልኝ» ብሎት የአዳሉ ንጉሥ ከየአለበት ሰብስቦ በፊቱ
ከአቀረበለት በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ዓምደ ጽዮን ተናዶ እያንዳንዳቸውን ሠላሳ (፴)
ጅራፍ እንዳስገረፋቸው በደረታቸውና በትከሻቸውም ላይ እንዳስከተባቸው በዚሁ
በጦርነቱ መጽሐፍ ተጽፏል (1) ።

ባሁኑ ባፄ ልብነ ድንግል ጊዜ ግን በወላስሞቹም መበርታት በግራኝ አህመ
ደም መነሣት ባለፈው በሰጠነው ዝርዝር ምክንያት እስላሞቹ እያየሉ ከፖርቱጋ
ሎቹ ጋር በተወጠነው ገምድና ምክንያት ከማይ ከዓረብ አገር እርዳታም እንደ
ልብ በብዛት እያገኙ በክርስቲያኖቹ ከመወረርና ከመገዛት አልፈው ባሁኑ ጊዜ
ደግሞ ከመውረርና ከመግዛት መድረሳቸው ነው ። የወላስሞች መደበኛ ከተማ
ይፋት መሆኑ ቀርቶ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. በኝሁ ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን ወደ ሐረር
እንዲዞር ማድረጋቸው ራሱ ወደነዚሁ ወደ ኢትዮጵያ የቅርብ አውራጃዎች ወደ
ባሌ ወደ ደዋሮ ለመቃረብና ለወረራ ምቹ ሥፍራ የመፈለግ አሳብ (ፕላን) ይመስ
ላል ። በዚሁም ጊዜ ከወዲህ በነርሱው ማባበል ጭምር አንዳንድ መኳንንት ቀድሞ
እየከዱ ወደነርሱ ይገቡላቸው የነበረው ባሁኑ ጊዜ ደግሞ እየባሰበት መሄዱን በዓ
ረብ ፋቂህ ጽሑፍ ላይ ይታያል ።
ISIC

ዓረብ ፋቂህ የባሌን ጦርነት በተረከበት መካከል ሲሙ ስለሚባለው የክርስቲ
ያን የጦር አሊቃ በተለይም ስለአባቱ ስለወናግ ገርን ከዳት ወደኋላው ተመልሶ ባፄ
ናዖድ ዘመነ መንግሥት የደረሰውን ሰፋ አድርጎ ጽፏል ።

ወናግ ዣን የስሙ ትርጓሜ የንጉሥ አንበሳ የራስ ወሰን ሰገድ ወንድም ነው ።
ራስ ወሰን ሰገድም ወደፊት ስለኢትዮጵያና ስለወገኑ ያደረገውን ተጋድሎ እንደም
ናነበው ከዓፄ እስክንድርና ካፄ ናዖድ ዠምሮ ከሹመት ወደ ሹመት እየተዘዋወረ
በቤተ መንግሥቱ የከበረ ታላቅ ሰው ነው ። ዳሞት ነጋሽ ጐጃም ነጋሽ እየተባለ
በየተራ ገዝቷል የቢትወደድነት ማዕርግም ይዞ ነበር ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በሽምብራ ኰሬ እነ ራስ እስላም ሰገድ በአይፈርስ ከተሸነፉ

(1) ወውእቱ ጊዜ ነደ ልቡ በመዓት ለንጉሥ ወአዘዘ ይዝብጥዎሙ ፴ ጥብጣቤ ሐብል ዓቢይ ወአጽ
ሐፈ ውስተ እንግድዓቲሆሙ ወውስተ መታክፍቲሆሙ . . . . . ገጽ 433 - 434

በኋላ ይህ ታላቅ ሰው በእንዴት ያለ አኳኋን ካለበት ከዳሞት መጥቶ ከግራኝ አህ መድ ጦር ጋር ተዋግቶ እንደሚሞት ወደፊት እናነባለን ።

ወንድሙ ወናግ ዣን ግን በጠባዩ ክዳት ደስ የሚለው ይሁን ወይም በሹመት ተቀይሞ ይሁን አለዚያም በወንድሙ ዕድገት ቀንቶ ይሁን በትክክል አይታወቅም ገና ባዬ ናዖድ ዘመነ መንግሥት አገሩንና ወገኖቹን ከድቶ ሐረር ሄዶ ሰልሞ ካሁኑ ሱልጣን ከኡመር ዲን አባት ከሱልጣን መሐመድ ጋር ተቀምጦ የወገኖቹን ጠላት ሲጠቅም የኖረ ነው ። ለዚህም ዋጋ ያገር ግዛት ተሰጥቶት በሚኖርበት ጊዜ ከእስላ ሞቹ ጋር በማበር ጦር ይዞ እየመጣ ብዙ ጊዜ ባሌን አዘርፏል ። ከዕለታት አንድ ቀን በባሌ ሲዋጋ የንጉሥ ነገሥቱ ጦር አሸንፎ ማረከውና እንደታሠረ ከንጉሥ ነገ ሥቱ ካዬ ናዖድ ፊት በቀረበ ጊዜ በከዳተኛነቱ ከፍ ያለ ቅጣት ሲገባው ሳለ ታማኝ ወንድሙ ራስ ወሰን ሰገድ አማልዶ አስፈታው ። ከዳተኛውም እንደ ታማኝ የባ ሌን ግዛት እንደገና ተሾሞ በክብር ቦታ ተቀመጠ ።

ነገር ግን ወናግ ዣን ከሐዲነት ከባሕርዩ ጋር የተዋሐደው ሰው ኖሮ ከውጊያ ላይ ማርኮ ከአሠረው በኋላ ሳይገድል ምሕረት ያደረገለትን ከዚያም አልፎ ታላቁን የባሌን ግዛት የሾመውን የራሱን መንግሥትና ንጉሡ ነገሥቱን ዓፄ ናዖድን መልሶ ከዳ ። በሹመት አገሩ ባሌ በነበረበት ሰዓት ከክህደት ጓደኛው ከድልበ ኢየሱስ (ድል በኢየሱስ ?) ጋር በመስማማት ከንጉሡ የመጣልኝ ትእዛዝ አለና ተሰበሰቡ ብሎ በባሌ የሚገኙትን ቁ[illegible]ቸው ፷ የሚደርሰውን ታማኝ የጦር አለቆቹን በቤቱ ሰብስቦ ብዙ ቀን የቆየ መጠጥ እየጋበዘ በማጠጣት ሰውነታቸውን ካደከመ በኋላ ወደ ውጭ ወጣ ብሎ እንግዲህ እነዚህን በእጃችን የጣለልንን ምን እናድርጋቸው ብሎ ለከዳት ጓደኛው ለድልበ ኢየሱስ ቢያማክረው እነዚህን እንደ በግ ማረድ ነው ብሎ መለሰለት ይባላል ። ከዚህ በኋላ ወናግ ዣን ከውጭ እንዳለ አሽከሮቹን ጠርቶ በሉ ግቡና ሁሉንም እንደ በግ እረዱዋቸው ብሎ አዞ ሁሉንም ባልጠረጠሩ በት ሰዓት አስፈጃቸው ።

ይኸንንም ሲያፍርበት የሚገባውን የጭካኔና የከሐዲነት ሥራውን ወደ ሱል ጣን መሐመድ ልኮ ፎከረበት ። ልጄን ሲሙን ልኮ ይኸውና እዚህ ያሉትን ሹማምንት አስፈጅቻለሁና ናልኝ ብሎ ሱልጣኑ ወደ ባሌ እንዲመጣለት ጋበዘው ። ስሞኑንም የቀረውን የባሌን ክርስቲያን እያስፈራራ ከክርስቲያንነት ወደ እስላም ነት ለወጣቸው ይባላል ።

የዚህ ወሬ ባዬ ናዖድ ዘንድ እንደተሰማ ስመ ጥሩው የጦር አለቃ አባ ገብረ እንድርያስ (የማኅፉዝ ገዳይ) ከንጉሣቸው ታዘው ወናግ ዣንን ለመውጋት ወደ ባሌ መጡና በሁለቱ መካከል ጦርነት ተዠመረ ። ወናግ ዣንም የተመካበትና የተ ፈራው ሱልጣን ሳይደርስለት ሦስት ቀን ያህል እንደተዋጋ መሸነፉን ሲያውቀው ጓዙን ሚስቶቹንና ዕቁባቶቹን ይዞ ወደ አዳል አገር ሲሸሽ ከመንገድ ሞተ የአሟሟ ቱን ሁኔታ ዓረብ ፋቂሀ አልገለጸውም ምናልባት አባራሪው አባ ገብረ እንድርያስ ወይም ከጦረኛው አንዱ መትቶት ይሆናል ።

ልጁ ሲሙ ያባቱን ጓዝ ይዞ ወደ አዳል ሲሄድ ሱልጣኑም በወናግ ዣን ጥሪ

መሠረት የሆነውን ሳያውቅ ወደ ባሌ ሲመጣ ከሲሙ ጋር በመንገድ ላይ ተገናኙ
ሡልጣኑም ሲሙን ይዞ ወደ ሐረር እንደተመለሰ የገራድነት ሹመት ሰጥቶ አስቀመ
ጠው ። ሲሙም ሰልሞ ቀድሞ አባቱ ወናግ ዣን ያደርገው እንደነበረ ወደ ባሌ
ከአዳሎቹ ጋር መጥቶ አገር ሲዘርፍ እንደገና በክርስቲያኖቹ እጅ ተማርኮ ጳሕፈ
ላም ተብሎ አሁን ባዬ ልብነ ድንግል ጊዜ ከእስላምነት ወደ ክርስቲያንነት ዞሮ ስለ
ነበረ በአሁኑ ሰዓት ግራኝ አህመድ ወደ ባሌ ሲመጣ ከነሸንቁር ጋር ተሰልፎ ግራ
ኝን ለመውጋት መጣ (1) ።

ይሁን እንጂ እንኳን ግራኝ አህመድ ሲቀናው እያየ ይቅርና እንዲያውም በደ
ኅናው ቀን ከሐዲነት ከላይ ከቤተ ሰቡ ተያይዞ የመጣ በመሆኑ ሲመቸው ከነጦሩ
ወደ ግራኝ ተገልብጦ እንደገና ወደ እስላምነቱ ዞሮ የገራድነት ማዕርግ አግኝቶ ግራ
ኝን ሲያገለግል ኖሮ በመጨረሻ ወደፊት እንደምንመለከተው በትግሬ አገር ረሃ
ብና በሽታ የተነሣ ጊዜ ሞተ ። እንደዚሁ በዚህ የመከራና የጦርነት ሰዓት ከሲሙ
በቀር ሃይቢ እናንያ ቴዎድሮስ የሚባሉት ወደ ግራኝ ዞረው ምሥጢር በመንገር
የጦር መላ በመስጠት መንገድ በመምራት ወገናቸውን እየበደሉ ጠላትን የጠቀሙ
ትን ወደፊት እናገኛቸዋለን ።

በ፲፱፻፳፰ - ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ አንዱ ባንዳ ሆኖ ወንድ
ሙን አርበኛውን ይወጋ እንደነበር አባቱ ለጠላት ታማኝ ሆኖ ልጁ በጫካ ስላገሩ
ተከላካይ አርበኛ እንደነበረው ዓይነት በግራኝ ወረራም ጊዜ በትክክል እንደዚሁ
ነበር ። ታሪክ በማናቸውም ጊዜ በየትኛውም አገር መልኩንና ሥራውን አይለው
ጥም ።

መቼም የአገር አከዳድ ነገር መንገዱ ብዙ ነው ። ከብዙው ውስጥ ዓይነተ
ኛው የሹመትና የደረጃ መዋረድ ነው ። ከዚህም ጋር በአገባብም ቢሆን ያላገባብ
አንዱ መኰንን በራሱ መንግሥት ውስጥ ጥፋት ተገኝቶበት ሲታሠር ወይም ሲገ
ረፍ ቁጭትና ጥቃት ገፋፍተው ወደ ጠላት ያስኮበልሉታል ። ወይም ነፍሱን ለማ
ዳን ወደ ጠላት ለመሄድ ይገደዳል ። ሙሉው ሥልጣን በእጃቸው ያለው አንዳንድ
ነገሥታት ደግሞ የየአንዳንዱን ሰው መብት እየጠበቁ በትክክል ይሾማሉ ወይም
ይፈርዳሉ ማለት አይቻልም ። በተለይ በዚያን ዘመን ያለ የየትም አገር ንጉሥ የራሱ
ሕሊና ካልወቀሰው ወይም ይሉኝታ ካልገታው በቀር እንደልቡ የፈቀደውን መሾም
የጠላውን ማሠር ወይም መግደል ይችላል ። በዙሪያው ካሉት ባለሥልጣኖች ውስጥ
አንዳንዶቹ በሥልጣን ላይ ያለውን ንጉሥ ተቆጥተው ከግፍ ሥራው ለመመለስ
እያንዳንዳቸው ከሥልጣናቸው ፣ ከሹመታቸው ተፈናቅለው ጉዳት እንዳይደርስባ
ቸው የንጉሡን ጥፋት በልባቸው እየታዘቡ በአፋቸውና በአድራጎታቸው የመጥፎ
ተግባሩ ደጋፊ ይሆናሉ ። ሊወቅስ የሚደፍር ቢኖር ምናልባት ትዳርና ሹመት ያል
ያዘ ፣ መነኵሴና ባሕታዊ ይሆናል ። የርሱም ወቀሳ በደፈናው ሲሆን ያውም የዕብድ
ወቀሳ ተብሎ ይዘለላል ። በዚህ ምክንያት ንጉሡ እንደልቡ በሚሠራበት ጊዜ ለጠ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 160 - 170

ISIC

ባዩ ያልተስማሙትን ብዙ መኳንንት ያላገባብ ሊያስቀይም ብዙውን ደግሞ በተለይ ዓይነ ሕሊናቸውን ጨፍነው የሚያገለግሉትን ሊያስደስት ይችላል ።

በሹመት በደረጃው ከፍ ያለው እየተደሰተ አገሩንና ንጉሡን ከልቡ ሲያገለግል የተጐዳው ወይም የእሥራትና የግርፋት ጥቃት የደረሰበት የጥቃቱን ጊዜ በትዕግሥት አሳልፎ ሌላ የመሾሚያ ጊዜና ዘዴ መፈለግ ወይም ሹመቱን መናቅ ያቃተው ቂጭቱን የሚወጣው ጊዜ ጠብቆ ወደ ጠላት በመደረብ ነው ። ስለዚህ ከሐረር ሡልጣን ተበደልን የሚሉት ወደ ነገሥታቱ እየመጡ በሹመት እያደጉ እዚያ የቀሩትን ሲያስቀኑ እንደዚሁም ከወዲህ ከንጉሡ የተጣሉት ወይም ክዳት ባሕሪያቸው የሆነ ክርስቲያኖች ወደ አዳል አገር እየገቡ የገራድነት ሹመት ካገኙ በኋላ ከአዳል ጦር ጋር እየመጡ በባሌ በደዋሮ አገር በመዝረፍ ወገኖቻቸውን በመግደል ቂጭታቸውን መወጣት የተለመደ ነው ።

ማናቸውንም የሕይወት ውዝግብ በልበ ሰፊነት ካላሸነፉት በጠባዩ ከመሠረቱ አገር አፍቃሪ የሆነው ሰው በቂጭት የተነሣ ከዳተኛ ለወገኑ አሳቢነት ያለው ባጋጣሚ ንዴት ጐጂ ሊሆን ይችላል ። ከሰው ግን ታላቅና መንፈሰ ብርቱ አገር አፍቃሪ የሚባለው የግሉን ቂጭት ባገር ክዳት ለመክፈል የማያስበው ነው ። በዚህ መካከል በሰላምም በጦርነትም ጊዜ ክዳት ደስ የሚለው በፍጥረቱ ለማንም የማይታመን አለ ። እንደዚህ ያለው ሰው በመንግሥቱ ምንም ዓይነት በደል ሳይደርስበት ወገኖቹን ለመክዳት[illegible]ር እስኪፈርስ የወገኑ ጦር እስኪሸነፍ አይጠብቅም ። በተረፈ ግማሹ ደግሞ እስከ መጨረሻ ከጠላት ጋር እየተዋጋ የሕይወቱን ፍጻሜ በጀብዱ ሽልሞ ለመሞት ያልታደለ የቆራጠኝነት ጠባይ የሌለው በደካማነቱ በቶሎ ካሸናፊው ጋር መለጠፍ የሚወድ ሞልቷል ። ተለጥፎም ዕድሜ ሳያገኝ በቶሎ የሚሞት አለ ።

ስለዚህ ባሁኑ በግራኝ ወረራ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ መሸነፍ የግራኝ ማሸነፍ ተስፋ ያስቀረጠው አድር ባይ የጦርነት ዕድል ካጋደለባቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ጉራ ገንጠል እያለ ጊዜ ላነሳው አሸናፊ እየገባ በማገልገል ወደፊት ያለውን ዕድሜውን ከጠላት ጋርም ቢሆን በመደሰት ሕይወቱን ለመቀጠል የሚመኘው በርክቷል ።

ነገር ግን ያገር ዋናው ጦር ከፈረሰ በኋላ በመንፈሳቸው ደካማነት የተነሣ በሚከዱት ላይ ታሪክ የሚሰነዝረው ወቀሳ ቀላል ቢሆንም የወገን ጦር ሳይሸነፍ ወገን ጦርነቱን በሚቀጥልበት ባሁኑ ሰዓት እንደ ክዱት እንደነ ድልበ ኢየሱስ ያለው እንደ ወናግ ዣን አምኖ የሾመውን መንግሥት አታሎ ወገኖቹን እንደ በግ አሳርዶ ለጠላት በመግባት መሣሪያ የሆነው ፍጹም ከዳተኛ በታሪክ ፊት ምንም ዓይነት ይቅርታ አይገኝለትም ።

## ምዕራፍ ፵፭

የግራኝ አህመድ አዳዲስ መሣሪያ ይዞ ከሐረር ወደ ደዋሮ መምጣት — በዓይፈርስ
ጦርነት ዋዜማ በእጅ አዙር የራስ ደገልሃን በራስ እስላም ሰገድ መለወጥ — ለዓይፈ
ርስ ጦርነት የሁለቱ ባላጋራዎች ዝግጅት ።

ግራኝ አህመድ ከባሌ ጦርነት ተመልሶ ወደ ሐረር ሔዶ ሁለት ወር ከቆየ በኋላ
እንደ ገና በአዲስ ዝግጅት ወደ ደዋሮ ተመለሰ ። ጦርነቱን ከዠመረ አንሥቶ ከአ
ሁን ጋር ከሐረር እየተመላለሰ አምስት ጊዜ መዋጋቱን አካባቢ ወደኋላው ተመልሶ
በየምዕራፉ በሰፊው ያነበበውን ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው አስታውሶ ሊገነዘ
በው ይችላል ።

፩ኛ. በመዠመሪያ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ራስ ደገልሃን ታሪከ ነገሥቱ መልአከ ኃይል
(የጦር አለቃ) የሚለው በደዋሮና በይፋት ጠረፍ ኤዲር በሚባለው ሥፍራ
ላይ ከአዳሎች ጋር ተዋግቶ አሸንፎ ዘርፎ ወዳገሩ በደስታ ሊመለስ ሲል
ግራኝ ከአቡበከር ቀጭኑ ጋር ተከታትሎ ደርሶበት ተዋግቶ አሸንፎት የተዘረ
ፈውን አስመልሶ ወደ ሐረር በደስታ ተመለሰ ። ከፋኑኤል ጋር ካደረገው ጦር
ነት ወዲህ ይኸ የመዠመሪያው የግራኝ አህመድ የድል ደወል የተሰማበት
ታላቅ ድምፅ ነው ። ከይሁና አምላክ ዠምሮ በየጊዜው በአዳሎች ላይ ሳያቋ
ርጥ ክርስቲያኖቹ ያገኙት ድል ስለአስተማመናቸው ዓይ ልብነ ድንግልና
የጦር አለቆቻቸው በዚህ የደወል ድምፅ የ151ጦ አይመስልም ።
ባመቱም በ፲፭፻፳ ዓ.ም. የግራኝ ዋና አዝማች በይፋት ወናግ ዣን በደ
ዋሮ አርባ ሺ.መልን አሸነፈለት ።

፪ኛ. በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በመስከረም ወር ከሐረር መጥቶ ባደቂ ላይ ከነራስ ማኅሀ
ንቶ ከነቢትወደድ ሠርፄ ጋር ተዋግቶ በአጋማሽ ከተሸነፈ በኋላ ፯ ወር
ያህል ሲዘጋጅ ሰንብቶ በሰባተኛው ወር በመጋቢት ወር በዚሁ ዓመት በ፲፭፻
፳፩ ዓ. ም. ሽምብራ ኰሬ ላይ ከርሱ የበረከተ ጦር የያዙትን ንጉሠ ነገሥቱን
አሸንፎ በድል አድራጊነት ሐረር ተመለሰ ።

፫ኛ. ከሐረር እንደገና በዚሁ ዓመት ወደ ደዋሮ መጥቶ አዝማች አቤልን አሸንፎ
ማርኮ በርሱ መሪነት ዋናውን የጦር መሪ ራስ ነቢያትን አባርሮ ብዙ ምርኮ
ካገኘ በኋላ በዚሁ በደዋሮ ተቀምጦ ወደፊት እየገፋ የቀሩትን የጦር አለቆች
እየወጋ ማስገበር ሲያምረው በአጠገቡ ካሉት አብዛኞቹ የጦር አለቆች አያቶ
ቻችንም አባቶቻችንም በአበሻ አገር ተዋግተው ያገኙትን ዘርፈው ይመለ
ሱ እንጂ በአገሪቱ ላይ የመቀመጥ ልምድ የላቸውምና እኛም እንቀመጥም
ብለው አሳቡን ስለተቃወሙት ለነርሱ ሲል ሳይወድ በግድ ወደ ሐረር ተመ
ለሰ ። ሐረር ሲደርስ ከነዚሁ ከሹማምንቱ መካከል ተለይተው ከሱልጣን
ኡመር ዲን ጋር ተባብረው እርሱን ከሥልጣን ለማባረር አድመው ተነሡ
በት ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ይኸን ሰውዬ ኢትዮጵያን ሊቀጣበት መድ
በት ኖሮ በዚህ አድማ ምንም ሳይጐዳ ሼኮቹ በመካከል ገብተው ከሱልጣኑ

ጋር አስታርቀዋቸው ሰላም ሆነና ጦርነቱን መቀጠል ቻለ ።

፬ኛ. በዚህ ምክንያት ከሱልጣን ኡመር ዲን ከታረቀ በኋላ በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ወደ ባሌ መጥቶ ከራስ ደገልሃን እንደራሴ ከሸንቁር ጋር ተዋግቶ አሸነፈ ። ከዋነ ኞቹ የጦር አለቆች አንዱን አቡበክር ቀጭኑን ወደ ቃግማ (ባሌ ውስጥ) ልኮ ለመያዝ በጥብቅ የሚመኘውን አዝማች ተክለ ሃይማኖትን አስማረከ ። ከን ጉሡ የምትዛመደውን ሚስቱን ለራሱ አግብቶ ምርኮኛውን ተክለ ሃይማና ትን እንደያዘ በደስታ ወደሐረር ተመለሰ ።

፭ኛ. አሁን ደግሞ ምርኮኛውን ተክለ ሃይማኖትን ወታደርና መሣሪያ በማቀበል ከሚረዱት የዓረብ አገሮች ውስጥ ላንዱ ለአያን ሱልጣን እንደመተያ ልኮ ከርሱ ወስዶ ያገባትን ሐጅራህን አስከትሎ በዚሁ ዓመት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ከሐረር ተመልሶ በደዋሮ በተለይ ዓይፈርስና አንጾኪያ ላይ ከነራስ እስላም ሰገድ መዋጋቱን እንመለከታለን ። የዚህን የዓይፈርስን ጦርነት ዓረብ ፋቂህ አንዳንድ ጊዜ የአንጾኪያ ጦርነት ይለዋል (1) ። ምናልባት በዚሁ ደዋር በሚ ባለው ታላቅ አውራጃ ውስጥ ምንም ያህል የማይራራቁ አንዱ ዓይፈርስ አንዱ አንጾኪያ የሚባሉ ሁለት ከተሞች ይኖሩ ይሆናል ።

ያዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ዓይፈርሲን ጠቅሶት ይገኛል ። በዚህም ላይ ከተማ ወይም ወረዳ መሆኑ አይታወቅም ። በዘመነ መንግሥታቸው መሐመድ አርዌ በድላይ የሸፈተ ISIC ያንደኛዩቱ ሚስታቸው የእቴጌ እሌኒ አባት የሐድያው ገራድ መሐመድ በማታለል ጭምር ለእርዳታ ልምጣ ብሎ ቢጠይቃቸው ወደኔ መምጣትህ ቀርቶ ዓይፈርስ ላይ ተዘጋጅተህ ጠብቅ ማለታቸውን ታሪክ ነገሥቱ ይገልጸል (2) ።

ነገር ግን ዛሬ የወረዳና የከተማው ስም በሁለት ልዩ ስም እንደሚጠራ ሳይሆን አብዛኛው ጊዜ ወረዳውና በላዩ ላይ ያለው ከተማ ባንድ ስም ይጠራሉና ዓይፈርስ በደዋሮ ውስጥ ያለ ያንድ ወረዳና በዚያው ወረዳ ውስጥ ያለው የከተማው ስም ጭምር ይሆናል ። አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች ይኸንኑ አገር ዓይፈር አምባ ብለውት ይገኛል ።

ይህ ዓይፈርስ የሚገኝበት ዋናው አውራጃ ደዋሮ ግን ከዚህ በፊት እንዳመለከ ትነው በፈጠጋርና በባሌ በሐረርና በይፋት ግዛት መካከል የሚገኝ ትልቅ አው ራጃ ነው ። ባገራችን ብዙ ወረዳዎች በያለበት ባንድ ስም እየተጠሩ ብዙ ጊዜ ጽሑ ፍን ሊያሳክሩ ይችላሉ ። ለምሳሌ ጃን አሞራ በትግሬና በሰሜን ውስጥ እንዳለ በሸዋ ውስጥ ጃናሞሬ (ጃናሞራ) አለ ። አማያ የሚባል አገር በወሊሶ በኩል እን ዳለ እንደዚሁም አንከበር አጠገብ አማያ አገር ጊዮርጊስ አለ ። በሸዋ ወረዳዎች

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 270
(2) ወሐድያ ገራድኒ ለአከ ኀበ ንጉሥ እንዘ ይብል . . . . . ቃለከ ኀቤየ . . . . . ወውእተ ጊዜ ለአከ ኀቤሁ ንጉሥን ዘርዓ ያዕቆብ እንዘ ይብል ለእመ እመጽእ ከመ እትራዳእከ ፊት ምጽእ ባሕቱ ንበርአ ሀገረ አይፈርስ ። የኢ.ት. ታሪክ ካዬ ይዙሩኖ አምላክ እስከ ዓዬ ልብነ ድንግል ዝየስ እት ምዕ. 35 ገጽ 186 - 188

የሚገኙ ስሞች በቤጌምድርና በትግሬ በጐጃምና በአማራ ሳይንት እንደዚሁም በጋላ አገሮች ይገኛሉ ። የዚህ ምክንያት አንዱ ሕዝብ በየምክንያቱ ወደሌላ አገር ሄዶ ሲሰፍር ስሙን በሰፈረበት ቦታ ስለሚተክል ነው ።

በዚሁ ዓይነት ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ያነሣነው ደዋሮ በ፫ ቦታ ይገኛል ። ሙሴ ቹሩሊ በታሪክ መጽሐፋቸው ደዋር በሚል ሥያሜ የሚጠሩ በኢትዮጵያ በሦስት አውራጃዎች እንደሚገኙ አመልክተዋል ፡ ፩ኛው እላይ የጠቀስነው ከባሌ በሰሜን ከሐረር በምዕራብ ፡ ከፈጠጋርና ከደፋት ደቡብ ያለው ነው ። ፪ኛው ከአውሳ ሰሜን ምዕራብ ከየጁ ወደ ምሥራቅ ሲል ያለው ፡ ፫ኛው በአሞ ወንዝ አጠገብ ወላሞ ጐን ያለው ነው (1) ።

አሁን እነራስ እስላም ሰገድ ሊዋጉ የሚዘጋጁበት አይፈርስ ያለበት ደዋሮ ግን በመዠመሪያ ቍጥር የተመለከተው በደፋትና በባሌ መካከል ባለው ደዋሮ ውስጥ መሆን አለበት ። በጉራጌና በአሩሲ መካከል ዛሬ በከምባታ ውስጥ የሚገኘውን የሐድያውን ባላባት ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ አይፈርስ ላይ ተዘጋጅተህ ጠብቅ ያሉት ስለ ዚህ ነው ። አንጾኪያ ይፋትና ኤፍራታ ውስጥ እንዳለ በዚህኛው ደዋር ውስጥ ሌላ አንጾኪያ የተባለ ዓይፈርስ አጠገብ ሊኖር ይችላል ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በሰላሙ ጊዜ በእስላሞቹም ሆነ ወይም በፈረንጆቹ ነጋዴ ዎችና መልክተኞች አማካይነት እንደምንም ብለው በትጋት የዘመኑን መሣሪያ ጠመንጃና መድፍ ገዛዝተው የሠለጠነ የጦር ሠራዊት ጓድ ሳያቋቁሙ በመቅረ ታቸው ፡ የወደፊቱም የአዳሎችና የሱማሌዎች ጦር[illegible]ባለፉት በረዥም ጊዜ ዓመ ታት አባቶቻቸው እነዓፄ ዓምደ ጽዮን ፡ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ካሸነፉበት ጦርነት የባሰ ሊመጣ ይችላል ብለው ባለመገመታቸው ፡ ገምተውም እንደሆነ በዚህ ዓይነት መመለሻውን አለማዘጋጀታቸው ስለሚታይ እነሆ በዚህ በሰላማዊና በዝንጋኤ ጊዜ ግራኝ አህመድ ደህና አድርጎ እየተዘጋጀ በመውጋት ተጠቀመበት ። ከቀይ ባሕር ማዶ ወደሚገኙት የሃይማኖት ወገኖቹ ወደ አደን ፡ ወደ ዘቢድ ፡ ወደ ጂዳህና ወደ ሐድራሞት ፡ ወደ መስቃን ሱልጣኖች ዘንድ እየተላላከ ከወዲህ በዘረፋ የሚያገኘ ውን ሀብትና ከብት ሰውም እንደ ተክለ ሃይማኖት ያሉትን ታላላቅ ሰዎች ሳይቀር በመላክ እያስደሰተ ተዋጊ ወታደርና የጦር መሣሪያ ጠመንጃና መድፍ ሲሰበስብ እርሳቸው በስንት ጣጣና ደጅ ጥናት እነዚያን ፖርቱጋሎች ተቀብለው ካሰናበቱ ወዲህ ሁኔታው እየተባባሰ ሄዶ እርሳቸው በሚገዙት ምሥራቃዊ ሰሜናዊና ምዕራ ባዊ ወሰን መውጫና መግቢያው በቱርክ ወይም እርሱ በሚገዛቸው በግብፅ ፡ በዓ ረብ ፡ በሱዳን ጦር ስለታጠረ የበቃና የሚያስተማምን መሣሪያ ማግኘት አልቻ ሉም ። በደቡብ ምዕራብ ያለውም ሕዝብ ከራሳቸው ሕዝብ የባሰ ምንም የሥልጣኔ ጮራ ያልፈነጠቀበት ሥልጣኔ በሌለው ባገር ተወላጅ ባላባት በጅምላ የሚነዳ ከጦር ፡ ከቀስት ፡ ከጕራዴ ፡ ከአንካሴና ከዱላ በቀር ምንም የለውም ።

(1) Studi Etiopici la storia e la Lingua di Harar ቍጥር 5 ገጽ 6 - 14

ተዋጊ ሕዝብ ፤ አዋጊ የጦር ሹም ፤ እህል ፤ ከብት ፤ ወርቅ እስኪበቃ ድረስ የተት ረፈረፈ አላቸው ። ዳሩ ግን ሁሉንም በትንሹ ሜካኒክነት ያለውን መሣሪያ የጨበጠ ትንሽ የቴክኒክ እውቀት ያለው ተዋጊ ስለሚበልጥ ኡስማን ባንዲት ጥይት የራስ ነቢያትን ጦር እንዳፈረሰው ማሰብ አለብን ። ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል በዚሁ በቀድሞው ከብዙ ሺ ዓመት ዝምድ ነዋሪ በሆነ የጦርና የጉራጌ ውጊያ በየ ለበት እየተዋጉም እያዋጉም ቢደግሙት ቢደጋግሙት የብዙ ጀግና ሕይወት ቢወ ዋበትም ከግራኝ ጋር የሚያደርጉት ጦርነት ከፍሬ ቢስነት አልዘለል ማለቱን ባለ ፈው እንደተመለከትነው ወደፊትም በሚቀጥሉት ምዕራፎች የበለጠ እንገነዘባ ለን ።

በተለይ በአሁኑ በአምስተኛው ጉዞ ወደ ታሪኩ ስንገባ እንደምናነበው ግራኝ አህመድ አዳዲስ መድፎች የዓረብና የቱርክ ወታደሮች ከቀድሞው ጨማምር ከመቼውም የበለጠ ተሰናድቶ ስለመጣ የአማራ ፡ የትግሬ ፡ የኢል ማያ (እሩሲዎ ችና ከምባታዎች ?) ወታደሮች ከነአለቆቻቸው ባዲስ ኃይልና ባዲስ ድርጅት ቢዋ ጉም ያልለመዱትና የማያውቁት የመድፍ ጥይት በትሩም ድምፁም በታትኖ አሸነ ፋቸው ።

ስለታላቁ የአይፈርስ ጦርነት በዋዜማው የተደረገውን ድርጅት ዓረብ ፋቂህ ከሚተርከው ውስጥ ፍሬ ፍሬውን ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«ይማም ከባሌ ጦርነት ከተመለሰና ሁለት ወር በሐረር ከቆየ ወዲህ አሳቡ ሁሉ እንደገና ወደ ሀበሻ አገር ለመዝመት ነበር ። ለማሸነፍ ወይም በዚያው ለመሞት እንጂ ከሁለት አንዳቸውን ሳይፈጽም ወደ አገሩ እንዳይመለስ በመሐላ ቆርጦ ነበር . . . . . ። ይኸንንም ከቆረጠ በኋላ ወደ ሀበሻ አገር ከመዝ መቱ በፊት ዘርባህ ወደሚባለው አገር ሄዶ ከሀርላህ ነገዶች ጋር ተገናኘ ። ወደዘይ ላም ሰው ልኮ የጦር መሣሪያ ሰይፍ ሌላም ሰበሰበ ። በሀበሻ አገር የሚዋጉትም መድፍ እንዲገዛ አዘዘ ። የሚፈልገውን ያህል ሁሉንም መሣሪያ ገዝተው አመጡለት ፡ ሰባት መድፍም በግዥ መጣለት ። ሰባ የሚሆኑ የማህራ ተወላጆች (1) ቅዱሱን ጦር ነት ለመካፈል መጡ ። አለቆቻቸው ሰይድ (ሳኢድ) ቤን ሳብን ኤል ማህሪ ፡ አህ መድ ቤን ሶለይማን ኤል ማህሪ ይባላሉ ። የሁሉም ጠቅላይ አለቃ ትልቁና የተከ በረው ሞሐመድ ቤን አሊ ማርዙቅ (ሙራዚቅ - ማርዛቅ) ነው ። እርሱም በደዋር ውስጥ በባብ - ሳሪ ላይ ሞተ . . . . . እንደዚሁም ለሱማሊዎች ለሀርላህ ነገዶች በየ ለበት ልኮ ነበርና ሁሉም ተሰበሰቡ ። በመዠመሪያ የሀብር ማጋዲ ነገድ በገራድ ዳውድ መሪነት ፱ ፈረሶች ፤ ፳፱ እግረኛ ፤ የመሬሃን ነገድ በአህመድ ቤን ሂራቡ መሪ ነት ፹ ፈረሰኛ ፺፱ እግረኛ ፤ ቀጥሎ የጎርጎራህ በገራድ አቢድ የጊሪ ነገድ በማታን መሪነት ፹ ፈረሰኛ ፡ ፩ሺ እግረኛ ፡ የዘርባህ ነገድ ከሀርላህ ተደርቦ በሱልጣን መሐ

(1) ማህራ በደቡብ ዓረብ የሚገኝ ተራራማ አውራጃ አንዳንድ ጊዜ ሽሀር ይባላል ከተሞቹ ሴሁት ኬሽን ይባላሉ ። ተቀማጩ ሕዝብ ከሐደዳን ልጅ ከማህራህ እንደሚወለዱ ያምናሉ . . . . . የባሴት ሬኔ ትርጉም ገጽ 170 - 171 የማስታወሻ ቍጥር 2 ።

ISIC

መድ መሪነት ፳ ፈረሰኛ ፫፻ እግረኛ መጡ ። ሌሎቹም እየገበሩ የገቡ እንደዚሁም የወዳጅ አገሮችም ሁሉም በደንብ ተሰበሰቡ ። በድምሩ ስንቅ ጫኝው ሳይቆጠር ፭፻ የፈረሰኛ ፤ ፲፪ሺ የእግረኛ ጦር ተሰበሰበ ። ይማም ድንኳኑን በሐረር አጠገብ አስተከለ የጎሬላ ሕዝቦች ማሞሊህ የሚባሉት ነገዶች ከወሰናቸው ላይ ካሉት ክርስቲያኖች ላይ የቀሙትን አርባ በቅሎዎች ለይማም ለጦር እርዳታ ሰጡት ። እነሱንም ፴ በቅሎ ጨምሮ ለማህራ ነገድ ሰጣቸው ።

ከዚህ በኋላ ይማም ወደ ሀበሻ አገር ለጦርነት ጉዞ ዠመረ። ከባሌ ጦርነት የተማረከችው ሐጅራህ የምትባለው የተክለ ሃይማኖት ሚስት የነበረችው ዕቁባቱ ተከትላው ነበር ። እንደዚህ ሆነው ጉዞ ከዠመሩ በኋላ ዚፋህ ከሚባል ከእስላሞች ግዛት ደረሱ ። የዚህ አገር ነዋሪ ሕዝብም እንደሀገራቸው ልማድ ጦር ሠራዊቱን አከብረው ጋብዘው አስተናገዱዋቸው ። ከዚያ አልፈው ..... ሺህ እሚባል ወንዝ ከዚያም አልፈው ራቡዳህ እሚባል ሥፍራ ደረሱ ። በዚያ ሳሉ ሸሪፍ መሐመድ ሐንዱል ፳ የእግረኛ ጦር ፫ መድፍ ..... ይዞ ደረሰ ። ከዚያ አልፈው ዲር (ኤድ - ዲር) ከሚባል ትልቅ ወንዝ አጠገብ ሠፈር ሆነና ሁሉም በየሠፈራቸው እያረዱ ሲበሉ ቁራን ሲደግሙ ..... አደሩ ። ከዚያ አልፈው የእስላሞችና የክርስቲያኖች አገር (ግዛት) ወሰን እሚገኘው ባቁልዛር ከሚባለው አገር ደረሱ (1) ።

ይማም አህመድ ሰንደቅ ዓላማዎችን አዘጋጅቶ አንዱን ባለጥቁር ቀለም ከድል በኋላ ኤሚር ለተባለው ለዓሊ ፤ ሁለተኛው ፲፭፻፩ አረንጓዴ ቀለም ለዘሀርቡይ መሐመድ ..... ባለነጩን ቀለም ሰንደቅ ዓላማ ለአውራይ አቡን ሰጣቸው ። እንደዚሁም አንድ ከድል በኋላ ወዚር ለተባለው ለኑር ቤን አብራሂም ፡ አንድ ለገራድ ኩሽም ፤ አንድ ለገራድ አህሙሽ ፤ አንድ ለገራድ ማታን ፤ አንድ ለአዶሌ ..... አከፋፈላቸው ። የራሱ የይማም ሰንደቅ ዓላማ ባለብጫ ቀለም ነው ።

የጦር ሠራዊቱም እሦስት ላይ ተከፈለና የሲምን ፤ የመሬሃንን ፤ የባርቱሪ (ሀብር ማጋዲን) ነገድ ያሉበትን አንዱን ክፍል ለወዚር አዶሌ ፤ ቀጥሎ ለሐርጋይ የሸዋን ፡ የኩሽምን ጓደኞች ለዚያው ላለቃቸው ለኩሽም ኑር ፡ የሁባትን ለገራድ አቡበከር ቀጢን ፤ የገዳያህን ለአውራይ ሺሃብ ኤድ ዲን አከፋፍሎ ሰጣቸው ። የመጨረሻው የጦር ክፍል ዝግና ኃይለኛ ያለበት ከሰይፋቸው ብዛት የተነሣ ባሕር የሚባሉት ከይማም አህመድ ጋር ሆኑ ።

እንደዚህ ሆኖ ከተደላደሉ በኋላ ከባቁልዛር ተነሥተው ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ አዋሽ አጠገብ ደረሱ ። በዚህ ጊዜ ይማም "የእስላም የጦር ሠራዊት ሆይ እነሆ ከወናግ ሰገድ ከክርስቲያኖች ..... ግዛት ደረስን የደዋሮ መንገድም እዚሁ አጠገባችን ነው ። ሌላዩቱ ወደ ወናግ ሰገድ ወደ ክርስቲያኑ ከተማ የምትመራን መንገድ ይቻትና ከሁለቱ የትኛዋን እንያዝ እስቲ አሳባችሁን ስጡ" ብሎ ተናገረ ። ኢሚር

(1) ያቄ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ብቁልዘር በሌላ ቦታ ባቁል ዘር ይለዋል ። «ወእምድኅረዝ ፈነውኮሙ ለሠራዊትየ ውስተ ኵሉ ምድረ ተንበላት እለ ይሰመይ ዙልኀረ ወግዳየ ኩበት ወፈድሲ ወሀርጋየ ወብቁልዘር ገጽ 283 ። ወመጽኡ ይጸብኡኒ እምወሰነ ፍንደቲ እስከ ወሰነ ባቁልዘር እለ ይብልዎሙ ወርጅህ ወገብል ገጽ 284 ።

ዘሀርቡይና ገራድ አህሙሽ ተነሥተው "ወደ ዋናዪት (ወደ ንጉሡ) ከተማ ወደ ባደቂ እንሂድና ከተማዋን እናጥፋት እርሷ ከወደቀች ሌሎቹ አውራጃዎች በጃችን ይወድቃሉ" ብለው ተናግረው ሲቀመጡ ፤ ወዚር አዶሌ በፋንታው ተነሥቶ «ይህ አሳብ መልካም አይደለም . . . . . በዠርባችን ደዋሮን ትተን ወደ ባደቂ የተጓዝን እንደሆነ የደዋሮ ሕዝብ ወርዶ አገራችንን ያጠፋል ። ይልቅስ በኛና ደዋሮ ባለው በክርስቲያኖቹ ጦር መካከል ብዙ ርቀት የለምና ሄደን ውጊያችንን በደዋሮ እንዠምር" ብሎ በተናገረ ጊዜ "የወዚር አዶሌ አሳብ የተሻለ ነው" ብሎ ሠራዊቱ እየተነሡ ተናገሩ ።

ስለዚህ ይማም ወዚር አዶሌን ከነጦሩ በአዋሽ በላይ በኩል ኤድ ዱባህ (የደዋሮ ሰሜን) የሚገኙትን ክርስቲያኖች እንዲወጋ ላከውና እርሱ ራሱ በዚሁ በአዋሽ ሠፈረ ። ወዚር አዶሌም የዱባህን አገር ዘርፎ የዘረፈውን ለአህመድ ልኮ ነበር ። አህመድም ለጦሩ አከፋፍሎ ወደ ደዋሮ ተጓዘና ደዋሮ ግዛት ገብቶ አርጎባ (፩) ደረሰ ። በደዋሮ የወሰን ሰገድ ልጅ ባሕር ሰገድ የሚባል ሹም ነበረ ። በፊት አባቱ ወሰን ሰገድ በደዋሮ ነበር በኋላ ግን ይማም አህመድ ከመምጣቱ አስቀድሞ ወሰን ሰገድ ልጁን ትቶ ወደ ዳሞት ሄዶ ነበር ።

የሀበሻ ንጉሥ የእስላሞቹን ወደ ደዋሮ መምጣት በሰማ ጊዜ ከደዋሮ በላይ መጥፎ ገደልማ በሆነው ዲል ማይዳ (የድል ሜዳ ?) በሚባለው ሥፍራ ጉድጓድ እንዲያስቆፍር ባሕር ሰገድ[illegible]ት ነበር ። ቀድሞ ሡልጣን መሐመድ ወደዚች አገር የእስላም ጦር ልኮ ያለቀው ብዙ ነበር . . . . . አሁንም ንጉሡ ባሕር ሰገድን ጉድጓድ እንዲያስቆፍር ያዘዘው በዚያው ዓይነት እንዲሆን ነው ። እርሱም ጉድጓዱን አሠርቶ በዘበኛ እያስጠበቀ ሲኖር በመካከሉ ሞተ . . . . . በርሱም ፋንታ አደሊህ (አዳሉ) የሚባለው የባሌ ተወላጅ ተሾመ ። እርሱም የባሌንና የደዋሮን ጦር ሰብስቦ ጉድጓዱን ሲጠብቅ ሳለ ይማም አህመድ የዚህኑ ወሬ ስለሰማ በአጠገቡ ያሉትን የክርስቲያን ምርኮኞች "ከዚህ ጉድጓድ ካለበት በቀር ሌላ መንገድ አታውቁምን" ቢላቸው "እምን እናውቃለን ነገር ግን እንተ ይኸን መንገድ ትተህ ወደ ሌላ ስትሄድ ጠላቶችህ አሁን አሉበት ሆነው ሊጠብቁህ አይችሉም" አሉት ። ከዚህ በኋላ ይማም ጦሩን እንደያዘ ጉዞውን ቀጠለ ። ግንባር ቀደም ለሆነውም ጦር ሱልጣን ቤን ዓሊን ሾመውና ጉብዝናቸው የታወቀውን ፩፻፶ ፈረሰኞች ይዞ ወደ ፊት እየተጓዘ ይመራ ዠመር ። በመካከል ይማም ከርሱ የማይለዩትን ጓደኞቹን ይዞ ዴል ማይዳ ደርሰው ሠፈሩ ፤ እስላሞቹ ጉድጓድ ያለበትን ትተው በሌላ መንገድ ማለፋቸውን ክርስቲያኖቹ በሰሙ ጊዜ የነበሩበትን ቦታ ትተው የሳሪን በር ይዘው ሠፈሩ። እስላሞቹም ወደ ሳድቃህ ድንጋይም ዛፍም ወደማይገኝበት ሥፍራ አቃንተው ሄዱ ። ወዲያና ወዲህም እያሉ እየባላገሩ ቤት ገብተው ስንቅ ሰበሰቡ ።

በዚያም ሳለ ይማም አህመድ ሰላይ ልኮ ነበርና ሰላዮቹ ተመልሰው ክርስቲያ

(1) በይፋትና በአንኮበር ውስጥ ያለው አርጎባ ከሐረር በታች ያለው አርጎባም ሊሆን አይችልም ፤ ምናልባት በዚሁ በደዋሮ ፪ኛ አርጎባ አለ ማለት ነው ።

ኖቹ በባብ ሳሪ መኖራቸውን . . . . . ነገሩት ብንከታተላቸውስ የሚዋጉ ይመስላች
ኋልን ቢላቸው አንተ ሙሉውን ጦር ይዘህ ብትሄድ ይሸሻሉ ያንድ ክፍል ጦር ብት
ልክ ግን መግጠማቸው አይቀርም አሉት ።

ስለዚህ ይማም ጦሩን በደንብ አሰለፈው ። ሁሉም ጦር በያለቃው ሆኖ ሰን
ደቅ ዓላማውን እንደያዘ ተሰልፎ ነበር ። በዚያን ጊዜ ይማም እንደዚህ ሲል ተናገረ
"እስላሞች ሆይ አዋሽ የነበርን ጊዜ ሁላችሁም ወደ ደዋሮ እንድንመጣ ፈቅዳችሁ
ነበር፤ይኸው እዚህ ከመጣን ወዲህ የሚዋጋን ጦር አላገኘንም ። ክርስቲያኖቹ ሊገጥ
ሙን አልቻሉም ከመዠመሪያው ላይ ክርስቲያኖቹን ጨረስናቸው አገራቸውን
ዘርፈን ሴትና ከብቶቻቸውን ማረክን ። አሁን በመሐመድ (ነቢዩ) እርዳታ በእስላም
ጸጋ ምንም አቅም የላቸውም ። ስለዚህ አሁን ወደ ሀበሻ ንጉሥ ወደ ወናግ ሰገድ
(ዓፄ ልብነ ድንግል) እንዝመት ምን ይመስላችኋል" ጦሩም "ለእግዚአብሔር፣
ለነቢዩ ለመሐመድና ላንተ እንታዘዝ ዘንድ ቅዱስ ጦርነቱንም ለማድረግ ቆርጠ
ናል የሀበሻውን ንጉሥ አለበት ድረስ ሄደን ለመውጋት እንንዝ" ብሎ መለሰለት
እርሱም "እግዚአብሔር ይባርካችሁ" ብሎ አመሰገናቸው ።

ከዚህ በኋላ እዚች ሥፍራ አንድ ቀን አድረው በማግሥቱ ጉዞው ተዠመረ ።
የግንባር ቀደሙና የኋላው ደጀን የማሕል ዘማቹ ከመድፍ ጋር በደንብ ተሰለፈ ።
ይማም የመካከለኛውን ፤ ወዚር አዶሉ ግንባር ቅደሙን ፤ ወዚር ኑር ደጀኑን ይመሩ
ነበር ። እንደዚህ ሆነው ተጉዘው ዋትማት ከሚባል ፩ፔሮራ ደረሱና በዚሁ ሥፍራ
ሳሉ ክርስቲያኖቹ አንጾኪያ ላይ መሥፈራቸውን ሰሙ ። እነሱም የእስላሞቹን መም
ጣት ሰምተው ቤተ ክርስቲያናቸውን ከቃጠሎ ለማዳን እቤተ ክርስቲያኑ ፊት
ለፊት ተሰልፈው ነበር ። የያዙትም ጦር ብዙ ነው ። የደዋሮ ሕዝብ በዚሁ ሥፍራ
እንደተሰበሰቡ ወደ ንጉሣቸው "እስላሞች ቤተ ክርስቲያንህን ሊያቃጥሉ ደን
ዛሉ" ብለው ልከው ነበር የወሰን ሰገድ ልጅ (ባሕር ሰገድ) ከሞቱ ወዲህ ወሰን
ሰገድ እስኪመጣ ድረስ ይኸን አገር (ደዋሮን) ከነወታደሩ ከነሹማምንቱ እንዲያገ
የተሾመው የባሌው አገረ ገዥ አዳሊህ (አዳሉ) ነበር ። ከዚያ በኋላ ንጉሡ ቢትወ
ደድ በድላይን (ምክትል) የጦር መሪ . . . . . ከሁሉም በላይ ጠቅላይ አዝማች የን
ጉሡን አማች ራስ ደገልሃንን ሾመ ። ደገልሃን መዠመሪያ የንጉሡን እኅት ወለተ
ቀለምሲስን አግብቶ የሠርጉ ለት ስለሞተችበት እኅቷን አመተ ውጥንን ያገባ ነው።
ቢትወደድ በድላይና ደገልሃን እስላሞቹን ለመውጋት ወደ አንጾኪያ መጡና አንጾ
ኪያ ካለው ከአዝማች አዳሊህ ጋር ተገናኙ ። ደገልሃን የበላይ ጠቅላይ አዛዥ ይሁና
ችሁ የሚለው የንጉሡ ደብዳቤ ተነበበና ሁሉም አሜን ብሎ ተቀበለ ።

እስላሞቹ ከዋትማት ተነሥተው ወደ ዓይፈርስ ለመሄድ አቀኑ በሁለቱ (ዓይ
ፈርስና ዋትማት) መካከል አራህ የሚባል ትልቅ ወንዝ አለ ። እርሱንም ለመሻገር
አንድ በታችኛው በኩል ብዙ ሰው የሚያውቀው አንድ በላይኛው በኩል ትንሽ
ሰዎች ብቻ የሚያውቁት ሁለት መንገዶች ነበሩ ። እስላሞቹ በታችኛው በኩል
ለመሻገር ቢሄዱ መንገዱ በክርስቲያኖቹ ጦር ተይዞ አገኙት ። በዚህ ጊዜ ሀይዳር
የሚባል እስላም "በላይኛው በኩል አንድም ሰው በማያውቃት መንገድ እመራ

ለሁ'' አለው ። ይማምም ፲፫ የሚሆኑ ምርጥ ፈረሶች ይዞ ወደዚያች . . . . . ተጓዘ ። መረውም መንገዱን ይኸውና ክርስቲያኖቹ እያጠብቁትም ብሎ ለይማም አሳየ ውና እርሱም ''እግዚአብሔር ይባርክህ'' ብሎ አመሰገነው ። ከዚህ በኋላ ይማም ወንዙን ተሻግረን የሌሊቱን ጊዜ እዚያ እናሳልፍ አለ ። ወዚርአዶሌ ከወንዝ ወዲህ አድረን ሲነጋ ተሻግረን ብንዋጋ ይሻላል ቢል ''መጥፎ አሳብ ነው ከወንዝ ወዲ ህማ ካደርን ክርስቲያኖቹ መኖራችንን ሰምተው ይህችኑ ክፍት መንገድ የዘጉ ብን እንደሆነ እዚያም እዚህም መሆን ይቸግረናልና ተሻግሮ ማደር ነው የሚሻ ለው'' ብሎ ይማም መለሰለትና ወንዙን ተሻግረው በላይ በኩል ሠፈሩ ። የቀረውም ጦር በመልእክት ሌሊት ደረሰና ከመጨረሻው ከደጀን ጦር ጋር አብድኢን ናስርና ዘሀርቡይ ኡስማን ማታ የመጨረሻው ጸሎት ከተደረገ በኋላ መድፋቸውን ይዘው ደረሱ ። መድፉም ወንዙን የተሻገረው በሰው ትከሻ ነው ። ሰዎቹም እፈረስ ላይ ነበሩ ። ሁሉም ተሻግሮ ሲያልቅ በዚሁ ወንዝ ማዶ በላይኛው በኩል ሠፈር ሆና ታደረ ።

ክርስቲያኖቹ የእስላሞቹን መሻገር ሲሰሙ ያሉበትን ሥፍራ ለቀው ወደ አን ጾኪያ ሄዱ ። እስላሞቹም የወንዙን ዳር ትተው ወደ አይፈርስ ሄዱ ። አዝማች ደገ ልሃን ፭ ቀን በአንጾኪያ ከቆየ በኋላ ለሚስቱ ለአመተ ውጥን በምሥጢር እንደዚህ ብሎ ላከባት ''ንጉሡ ወንድምሽ የጦር ሠራዊት አዝማች አድርጎኛል ። ነገር ግን ከእስላሞቹ የምዋጋበት ፩፻፸ የለኝምና ስዋጋ የሞትሁ እንደሆነ አንቺም ያለባል ፥ ልጆችሽም ያለአባት ይቀራሉ ። ስለዚህ እኔ የላክሁሽ ሳታስመስይ ንጉሡን አማል ደሽ ወደኝቱ እንድመለስ አድርጊ'' ።

ሚስቱም ከሌሎቹ አለቆች በድብቅ ወደ ንጉሡ ገባችና ''አማችህን ከእስላ ሞች ጋር እንዲዋጋ ላክኸው የገደሉት እንደሆነ እኔ ያለባል ልጆቹም ያለአባት መቅረታቸው ነውና በርሱ እግር ሌላ የጦር አለቃ ሹምና እርሱ ወዳንተ እንዲመጣ ላከበትና እፊትህ እየተዋጋ ይሙት'' ብላ ለመነችው ። ንጉሡም በእርሱ እግር የፈ ጠጋሩን አገረ ገዥ አዝማች እስላሞን ሾመና ለአዝማች ደገልሃን እንዲመለስ ላከ በት ። አዝማች እስላሞ ብርቱ ተዋጊ ነው ። ደገልሃን መልእክቱ ሲደርሰው ሌሊ ቱን ከአንጾኪያ ወደ ንጉሡ ሄደ ። በማግሥቱም እስላሞ በመርዘኛ ቀስት የሚዋጉ ትን የኢልማያን ነገዶች እንዳስከተለ አንጾኪያ ደረሰ ። እነዚህም ነገዶች አገራቸ ውና ከሱማሌ አገር ከ ሚበቅል ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ቀስትና ፍላጻቸውን አበጅተው ጫፉ እንዲጠነክር ሥሩን በእሳት እያቃጠሉ ያበጁና በርሱ የመቱ እንደሆነ የተመ ታው ሰው ወዲያው ጠጉሩ ይቃጠልና በመርዙ ይሞታል . . . . . .» ሲል ዓረብ ፋቂህ ከውጊያው በፊት ያለውን የግራኝን ጉዞና ዝርዝር ድርጅት በወዲህም የክርስ ቲያኖቹን ሁኔታ ያመለክታል (1) ።

ለዚህ ጦር ጠቅላይ አዝማች ሆኖ እንዲዋጋ የታዘዘው እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻ ጻፍ የንጉሡ አማችና የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ደገልሃን ኖሯል ። ነገር ግን ይህ የጦር

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 170 - 181

እለቃ ባንድ ወገን ከዚህ በፊት በ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ከግራኝ ጋር በራሱ መሪነት ተዋግቶ በሽምብራ ኩሬም ጦርነት የደረሰውን ስለሚያውቅ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ግራኝ አዳዲስ መድፎች አስጭኖ ከመቼውም የበለጠ ተዘጋጅቶ መምጣቱን በሰላዮቹ በኩል ስለተረዳው እኔን የላከ ሳታስመስይ ለንጉሡ ንግረሽ እንድመለስ አድርጊኝ ብሎ ለሚስቱ ለአመተ ውጥን መላኩ የግራኝ አያያዝ አስፈርቶት ለመሆኑ አይጠረጠርም ። ምናልባት ለግል ሕይወቱ እንኳን ባይሳሳ ከዚህ በፊት በ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. እንደደረሰበት በርሱ መሪነት ጦሩ ተሸንፎ ተበተነ ወይም ሸሸ ከምባል በዚህ ዓይነት እኔ ተለውጬ የድሉን ሃፍረት ሌላው ይሸከመው ቢቀናውም ክብሩንም እርሱ ይውሰደው ብሎ ይሆናል ።

ምትን ወይም ውርደትን ወይም ሁለቱንም ፈርቶ በሚስቱ ምሥጢራዊ መልእክት በተለወጠው በራስ ደገልሃን እግር የዓይፈርስን ጦርነት በበላይ አዛዥነት ሊመራ የመጣው ዓረብ ፋቂህ ባጭር ስሙን "እስላም" ያለው ራስ እስላም ሰገድን ነው ። የዚህም ከፍተኛ መኰንን ዝርዝርም አጭርም የሕይወት ታሪኩ ባይኖረንም በስሙ አጠራር ከፍተኛ የዝግንነት ሞያ ያለው ምናልባት እስከዚህ ድረስ በውጊያ እስላሞችን ሲያጠቃ የኖረ በእስላሞች ዘንድ የተፈራ ይሆናል ። እስላም ሰገድ "እስላምን የሚያሰግድ" መባሉም ከዚሁ ከዝግንነቱ ጋር በተያያዘው የፈረስ ስም ይሆናል ።

ታላቅ ሰው መሆኑንም የገበዘ አክሱም መዝገብ ማይ ወይን ትባል ለነበረው ISIC በኋላ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጉባኤ ማርያም ብለው የምድረ እስጢፋን መሬት የጉልቱን ዓፄ ልብነ ድንግል ሳዶ ገዩ በነበሩበት ጊዜ አድሰው ባጸደቁት ላይ የነበሩትን ሲዘረዘር የሲሬ (ሺሬ) ሹም ረዳእ ካለ በኋላ የቀኝ ቢትወደድ እስላሙ የግራ ቢትወደድ ወሰን ሰገድ ብሏል ። ከዚያ እልፍ ብሎ በሌላ ቦታ ለአባ ተንሥአ ክርስቶስ በተንቤን ሀገራይ ድራዕ ድርባ የተባለውን ቦታ መካነ ሥላሴ ባሉበት ጊዜ ሲተክሉና የነበሩትን ሲቆጥሩ አዛዥ ሠርፄ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ የሐፄ እናት (እናታቸው) ናዖድ ሞገሳ ይልና የግራ ቢትወደድ ወሰን ሰገድ የቀኝ ቢትወደድ እስላም ሰገድ ይላል ። በዚሁ በቀኝ ቢትወደድነት ደረጃ በሌላም ሥፍራ ያነሣዋል (1) ።

ከርሱ ጋር ዓረብ ፋቂህ ባንድ ቦታ ቢትወደድ በድላይን በራስ ደገልሃን ሥር ሆኖ ለዘመቻ መምጣቱን በሌላ ቦታ ደግሞ ወደፊት እንደምናነበው በደገልሃን ምትክ ራስ እስላም ሰገድ የበላይነት ተሾሞ በመምጣቱ በድላይ ተቀይሞ ወደ ሻርካህ መሄዱን ይገልጻል ።

የዚህ የጦር መኰንን ስም እንደዚሁ በገበዘ አክሱም መጽሐፍ ራስ ወሰን ሰገድና ራስ እስላም ሰገድ የቀኝና የግራ ቢትወደድ ከተባሉበት ላይ ከቢትወደድ

(1) መጽሐፈ አክሱም ዘሀገር ወገበዘ አክሱም ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 27 ቍጥር 21 ገጽ 29 ቍጥር 26 ገጽ 30 ቍ. 27 - 28
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 177 . 192

ሠርጼ ጋር ግራና ቀኝ ሆኖ መሥራቱን መዘገቡ እንደዚህ ሲል ጠቅሶታል "በአኩ ቴተ አብ . . . . . እኔ ወናግ ሰገድ ስመ መንግሥቴ ዳዊት ስሟ ምምሳሕ ለተባለው ለእናቴ ለእግዚእ ክብራ ጉልቷን አድሻለሁ ፡፡ የነበሩ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ግራ ቢትወደድ ሠርጼ ቀኝ ቢትወደድ በድሉ አዛገሮች ደገልሃንና ዕንቋ" በዚሁ ዓይነት በብዙ ቦታ ተጽፎ ስለሚገኝ ቀደም ብሎ እርሱ ቢቶደድ ሆኖ ደገልሃን አዛዥ በመ ሆኑ በማዕርግ በድሌ (በድላይ) ደገልሃንን ይበልጠው ነበር ማለት ነው (1) ፡፡

ምናልባት ደገልሃን የንጉሡን እኅት አመተ ውጥንን ካገባ በኋላ በዚሁ ጋብቻ የተነሣ በማዕርግ በልጦት የታገሠውን አሁን ደግሞ ጓደኛው እስላሞ (እስላም ሰገድ) በበላይ ሆኖ ሲመጣ ፈጽሞ ትዕግሥቱ አልቆ ቅያሜውን ገልጿል ማለት ነው ፡፡

ስሙን የገበዘ አክሱም መጽሐፍ በድሌ ሲለው የዚህ ዓይነቱ የስያሜ ቅርጽ በድል ሰገድ የተባለውን አሳጥሮ በመጥራት ይመስላል ፡፡ እርግጥ መሆኑ አይታወ ቅም ፡፡ ይኸውም እስላም ሰገድ ባጭሩ እስላሞ ደገልሃን ዴገል ይባላል ፡፡ ዓረብ ፋቂህ በድላይ ሲለው ስሙን ከዚህ በፊት ካዬ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር ተዋግቶ ከተገደ ለው ከአርዌ በድላይ (2) ጋር ስለአጋጠመው ይህ ሰው ከወላሰሞች የዘር ግንድ ዝምድና እንዳለው አይታወቅም ፡፡

የሆነ ሆኖ ግራኝ ከሐረር በደንብ ተዘጋጅቶ ቀድሞ የሌለውን አዳዲስ መሣ ሪያና መድፍ ይዞ በጉ[illegible]መጣና በክርስቲያኖቹ ዘንድ ደገልሃን በእስላም ሰገድ ተለውጦ ከተመለሰ በኋላ በሁለቱ ጦር ሠራዊት መካከል የተደረገውን ጦርነት በሚቀጥለው ምዕራፍ እናነባለን ፡፡

## ምዕራፍ ፴፮
## ዓይፈርስ ላይ በራስ እስላም ሰገድና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገ ጦርነት (የካቲት ፲፭፻፳፫ ዓ. ም.)
## ከግራኝ ጋር ያሉት መድፎች ‧ የቢትወደድ በድላይ ቅያሜ ፡፡

ከመሣሪያው ከተዋጊው ብዛት ጋር የአይፈርስን ጦርነት ታላቅነት የምንረዳው የቀ ሩትን ጦርነቶች ሁሉ ትቶ እንደሽምብራ ኩሬ የአይፈርሱንም ጦርነት ታሪክ ነገሥ ታችን ባጭሩም ቢሆን ስለጠቀሰው ነው ፡፡ በራስ እስላም ሰገድ መሪነት አይፈርስ ላይ በአዝማች ተክለ ኢየሱስ አዝማችነት ዛሬ ላይ የተደረገውን ሁለቱን የተለያየ ጦርነት ታሪክ ነገሥቱ ባንድነት አጣምሮ ከሽምብራ ኩሬው ጦርነት አከታትሎ

(1) መጽሐፈ አክሱም ገጽ 36 ቍ. 40 ገጽ 37 ቍ. 41 ገጽ 38 ቍ. 42
(2) ሺሃብ ኤድ ዲን በድላይ (አርዌ በድላይ) ያዬ ዘርዓ ያዕቆብና ያዬ በዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ 20 - 21

በመካከል በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. በደዋሮ በባሌ የተደረገውን የነራስ ነቢያትን የነፋኑኤልን የነተክለ ሃይማኖትን ጦርነት ዘሎ ይመጣና ስለ አይፈርሱ ጦርነት ብቻ እንዲህ ይላል «ያገሩ ሰዎች እንደነገሩን በሁለተኛው ዓመት በጥር ፲፯ ቀን ከአዳል (ሐረር) ተነሥቶ በየካቲት ፲፱ ቀን ደዋሮ ደርሶ በሚያዝያ ፳ ቀን በአይፈርስ ጦርነት አድርጎ ራስ እስላም ሰገድና ተክለ ኢየሱስ ሌሎችም ብዙ መኳንንት ሞቱ ፤ ከዚያ በኋላ ሸዋን ገዛት» (1) ።

ታሪከ ነገሥቱ በዚህ አነጋገር የሚያሳየን ግራኝ አህመድ ባሌን ወግቶ ወደ ሐረር ከተመለሰ በኋላ እንደገና ከሐረር በጥር ፲፯ ቀን ተነሥቶ በየካቲት ፲፱ ቀን ደዋሮ ገብቶ በሚያዝያ ፳ ቀን አይፈርስ ላይ ጦርነት ማድረጉን በጦርነቱም ላይ ራስእስላም ሰገድና አዝማች ተክለ ኢየሱስ ሌሎችም ብዙ መኳንንት ማለቃቸውን ከነወሩ ከነቀኑ ይገልጽና የዝሆን ዱሩን ጦርነት ዘሎ ወደ ደብረ ሊባኖስ ቃጠሎ ይራመዳል ። ሲጽፍም የዚያ አገር ሰዎች እንደ ነገሩን ስለሚል ደራሲው በጦርነቱ ላይ ያልነበረ መሆኑን ያመለክታል ። ምናልባት ያፄ ልብነ ድንግል ዘመን አልፎ ሰላም በተመሠረተበት ዘመን እየጠየቀ ጽፎት ይሆናል ።

ከ፪ ዓመት በኋላ የሚለው ከ፲፭፻፳፭ ዓ. ም. ከሽምብራ ኩሬው ጦርነት ዠምሮ መቁጠሩ ስለሆነ የአይፈርስ ጦርነት በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. መሆኑ ነው ። ይኸም ዓረብ ፋቂህ እንደ እስላሞቹ የሒጅራ አቈጣጠር ረጀብ ፱፻፴፯ ያደረገውን ሙሴ ሬኔ ባሴት ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. እንደ አ. አቈጣጠር ስላደረገው በኛ ያው ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. ይሆናል (2) ።

አሁን ከግዕዙ ታሪከ ነገሥት ሰፋ አድርጎ የሚተርክልንን የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ምንም እንኳን በአጻጻፉ ወገኖቹን እስላሞች እያገነነ እያሞገሰ ክርስቲያኖቹን በሙሉም ባይሆን በገሚስ ማኮሰሱን ባንስተው የታሪኩ ጠቃሚነት ጉልህ ስለሆነ በዚህም ላይ የዚህን ጦርነት ታሪክ የሚተርክ ሌላ የማማረጫ ጽሑፍ ስለ ሌለ ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«እስላሞ (ራስ እስላም ሰገድ) ይዞ የመጣው ጦርና እንጾኪያ የነበረው ጦር ከመንገድ ላይ ተገናኙ ። እስላሞም የጦሩን ብዛት . . . . . ባየ ጊዜ ደስ አለው ። እርሱም ቀድሞ ጾሞት የነበረ ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ከእስላሞች ጋር ተዋግቷል . . . . . ሁለት ቀን እንጾኪያ እንዳደረ በሦስተኛው ቀን እስላሞቹ ከእንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ግርጌ አደሩ ። ሲነጋ ይማም አውራይ አቡበከርን ወዚር መሐመድንና ሌሎችንም ከ፺ ፈረሰኞች ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ላካቸው ። ከክርስቲያኖቹ ውስጥ

(1) ወእምዝ በ፪ቱ ዓመት ፲ወ፯ ለወርኃ ጥር ተመይጠ ወተንሥአ (ግራኝ) እምብሔረ አዳል ወበጽሐ ደዋሮ አመ ፲ወ፱ ለየካቲት በከመ ነገሩነ ሰብአ ውእቱ ብሔር ወገብረ ፀብዓ (በአይፈርስ ?) አመ ፳ ለሚያዝያ ወሞቱ ራስ እስላም ሰገድ ወተክለ ኢየሱስ ወብዙኃን መኳንንት ወመለካ ለሸዋ ። ሬኔ ባሴት ያሳተመው ታሪከ ነገሥት ገጽ 327 ። ጋሪስ የተቀመጠው ገጽ 92 ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 186

ዓይተዋቸው ተደብቀው እስኪጠጉ ድረስ ዝም ብለው አልፈው ይጠብቋቸው ዠመር ። እስላሞቹ የጠላቶቻቸውን መኖር ሳያውቁ ቤተ ክርስቲያኑን ሲመለካከቱ ክርስቲያኖቹ በድንገት ደርሰው ውጊያ ዠመሩዋቸው . . . . . እስላሞቹም ጥቂት እንደተከላከሉና ሁለት ፈረሰኞቹ ተመትተው እንደወደቁ የቀሩት ወደ ሠፈር ሽሽታቸውን ያዙ ። እመንገድ ሲደርሱ እነ ሲዲ መሐመድ ዓሊ ጉይታ ፡ እነ ታኪያ . . . . . ያሉበት ሌላ ጦር አገኛቸውና ወዴት ትሸሻላችሁ እኛ የምንመጣው እናንተን ለመርዳት ነው ብለው ተመልሰው እንዲዋጉ ለመኑዋቸውና ባንድነት ሁሉም ተመልሰው እነዚያን ክርስቲያኖች ውጊያ ገጠሟቸው ። እነዚያም ከዚያ ሸሽተው ወደ ዋናው ሠፈራቸው ሄዱ ።

እስላሞቹም ተመልሰው ይኽንኑ ነገሩት እርሱም (ግራኝ) "ወዴት ነው ክርስቲያኖቹ የተሰለፉት ከቤተ ክርስቲያኑ በላይ ወይስ በታች" ብሎ ጠየቀ ። ሰዎቹም "አዝማች እስላሞ ከቤተ ክርስቲያኑ በላይ ደርሶ የእግረኛ ጦሩንና ፈረሰኛውን በጫካ ውስጥ አሰልፏል ። አዝማች አቤት (አበብ ፡ አቤት ?) ግን እኛ ወደ ራስ እስላሞ ጦር ስናቀና ከቤተ ክርስቲያኑ በስተግራ በኩል ሆኖ ከኋላችን ድንገት ደርሶ አደጋ ጣለብን ብለው ነገሩት ። አቤት ይማም አራን (አርአን) አገር የነበረ ጊዜ እን ደዚህ ብሎ ደብዳቤ ጽፎለት ነበር ። "ጦርነት በየጊዜው ይለዋወጣል (1) በሽምብራ ኩሬ ጦርነት እግዚአብሔር ረድቶህ ጦራችንን ሁሉ ፈጀህ አርበኞቻችንንም በታተንህ ። አሁን ግን እስካሁን ያደረግኸው ይበቃሃልና ብትተወን ይሻላል ያለዚያ ግን እግዚአብሔር እንደ ሎጥ ከተማ ያጠፋሃል ፤ አትኩራ" (2) ።

ይማምም እየሣቀ "ተመልከቱ ዛሬ በተንኮል አደጋ ጥሎ የወጋን አቤት በፊት ይኽን ደብዳቤ ጽፎልኝ ነበር አሁንም ወደ እስላሞ ብንሄድ ከኋላችን አቤት ይወጋናል ። ወደ ርሱ ብንዣዝ እስላሞ ይወጋናል ምን ይሻላል" ብሎ ለወገኖቹ አማከረ ። በዚያን ጊዜ ወዚር ኑር እንዲናገር አስፈቅዶ ብድግ አለና "ጦርነት የሚፈጸመው በተንኮል ነው ። አሁንም በተንኮል ተደብቀው የሚዋጉትን ክርስቲያኖች ብዙ ሆኖ መመለስና ወደ ወገኖቻቸው ወደ ዋናው ጦር እንዲደባለቁ ማድረግ ነው" ብሎ ተናገረ ። ይማምና ጓደኞቹም መልካም ምክር አመጣህ አሉት ። ከዚህ በኋላ ይማም" መልካም ነው አንተ ከነጦርህ ወደነሱ (ተደብቀው ወደሚዋጉት ወደነ አቤት) ሂድ እኛ ደግሞ እስላሞን እንወጋዋለን" ብሎ ለወዚር ኑር ነገረውና ኑርም እሺ አለ ። ስለዚህ የታወቁ የፈረሰኞች አርበኞች እነአቡበከር ቀጢን ፤ እነኤሚር ዓሊ ፡ እነገራድ አህመድ . . . . . እነሸሃብ ዲን . . . . . . እነ አውራይ ኡመር ዲን . . . . . , ያሉበትን መቶ የፈረሰኛ ጦር ሰጠውና ኑር ወደዚያው በድብቅ ወደሚዋጉበት ዘንድ ሲሄድ ይማምና የቀረው ጦር ወደ እስላሞ ዘንድ ተጓዙ ። የጦሩ ሠልፍ ያማረ ነበር ። ዓረቦቹ ከፊት ሆነው ከበሮ እየመቱ እምቢልታ እየነፉ መድፉ ፊት

(1) ረኔ ባሴት እንደሰጠው አሳብ ጦርነት እንደውሀ መቅጃ አንዳንድ ጊዜ ይወጣል አንድ ጊዜ ወደ ጉድጓድ ይወርዳል ለማለት ነው ። ዓረብ ፋቂህ ገጽ 182 ።

(2) እንደ ሎጥ ሚስት ወይስ እንደከተማው ሰዶም ዘፍጥ ምዕ. 19 ቍ. 26

ለፊት ይንገ ነበር ። እስላሞቹ እፈረስ ላይ ወጥተው ጥሩራቸውን ለብሰው የእግዚአ ብሔርን ታላቅነት የነቢዩን ሐዋርያነት ገልጸው . . . . . ለጦርነት ተሰለፉ ።

ክርስቲያኖቹም እንደዚሁ ተሰለፉ ። ቍጥራቸው ፮ሺ የፈረሰኛ ፩፻ሺ የሚያህል የግረኛ ጦር ሳይሆን አይቀርም ቍጥሩን እግዚአብሔር ይወቀው ። የእስላሞቹ ግን ተቆጥሮ ፭፻ ፈረሰኛ ፲ሺ የእግረኛ ጦር ነበር ። ሁለቱ የጠላት ጦር ተቀራርቦ ይተ ያይ ዠመር ። ይማም ድንኳኑን አስተከለ ። ከዚህ በኋላ አንድ ጊዜ እስላሞቹ በክር ስቲያኖቹ ላይ አንድ ጊዜ ክርስቲያኖቹ በእስላሞቹ ላይ እየገሠገሡ ይዋጉ ዠመር ። ጦርነቱም እስከ አሥር (ሰዓት) (1) ቆየ ። የባሌ ጦር ወዚር ኑር ያለበትን የቀኙን አዝማች ጦር እየደጋገመ ወግቶ እየገፋ እስከ ይማም ጦር ድረስ አደረሰው ። ይማም አህመድም "እርሱ የምትዋጉበት ሥፍራ ለውጊያ ምቹ አይደለምና አትዋጉ ዝም ብላችሁ አላችሁበት ቦታ እርጉ" ብሎ በቁጣ ቃል ነገራቸው ። ማታንና ሁሴን ቤን አብደላ ሌሎችም ከእስላሞቹ በግራ በኩል ሆነው ሲዋጉ ይማም በማታን ላይ ተናዶ ልኮ አሲዞ እፊቱ አስመጣና "ተዋጋ ብሎ ማን አዘዘህ አርፊህ መቀመጥ አይሆንልህምን" ብሎ ተቆጥቶ እንዲያርፍ አደረገው ።

የይማም ጋሻ ዣግሬ ከቢር ኑር ከማታን ጋር ሆኖ በሚዋጋበት ጊዜ አንዱን የባሌ የጦር አለቃ በፈረስ ሲጋልብ በቀስት ለመምታት ቢወረውር እርሱን ስቶ ፈረሱን መታና ጣለው ። አለቅየውም በግሩ ሮጦ ወደ ወገኖቹ ተደባለቀ ። ይማም ሥፍራችሁን ዝም ብላችሁ ያዙ እንጂ አትዋጉ ብሎ አዘዘ ። የባሌው የክርስ ቲያኖች ጦር ግን የላይኛውን ክፍል ይዞ በግራም በቀኙም ያለዕረፍት እየተዋጋ እታች በሚገኙት እስላሞች ላይ ብዙ ጉዳት አደረገ ። እስላሞቹ እግራቸውን መሬት አሲዘው የሚዋጉበት ምቹ ሥፍራ አላገኙም ነበር ። ስለዚህ ይማም ኤሚር ዘሀር ቡይ መሐመድን ፤ አህመድ ጎይታን ፤ ኤሚር ዓሊን ፤ ገራድ አህመድን ፤ ኤሚር አቡ በከር ቀጢንን ፡ ታኪያን . . . . . አሥር የሚሆኑትን ጉበዛዝት ፈረሰኞችን ከመ ድፍ ጋር አስመጣና አንዱን መድፍ አሲዞ የባሌ ወታደር ወደሚዋጋበት አመራ ። በዚያም የዓረብ አገር የማህራህ እግረኛው ጦር ከእግረኛ ጦር ጋር ሲዋጋ በጉን በኩል ደርሶ ከዓረቦች ውስጥ አል ዐጅ መሐመድ የሚባለው የማግረብ ተወላጅ ተኩሶ ያንዱን የክርስቲያን እግር ሰበረው . . . . . አህመድ ወደ ጦርነቱ ሥፍራ በደረሰ ጊዜ የዓረቦቹን (የመድፈኞቹን) አለቃ ሰይድ ቤን ሳባንን ከአንድ መድፍ ጋር አጠገቡ ጠራና "መድፍህን በሚዋጉት ክርስቲያኖች ላይ ተኩስ ፤ ከዚያ ቀጥ ለን እኛ ገሥግሠን ውጊያውን እንገጥማቸዋለን" አለው ።

ስለዚህ አለቅዩው መድፉን እመሬት አድርጎ ወደ ክርስቲያኖቹ አስተካክሎ አነጣጠረና ቢተኩሰው በክርስቲያኖቹ መካከል የነበረውን የወይራ ዛፍ እሁለት ጉመደው ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኑ አንዱ ባንዱ ላይ ተነባብሮ ወደቀ ። ይማም "ይኸን ጊዜ እንውጋቸው" አለና ከፈረሰኞቹ ጋር ጋልቦ የመለሳይንና የማህራን

(1) አሥር ይላል እንጂ ሰዓትን አይጨምርም አሥር ሲል የአሥር ሰዓትን ወይም የተሲያት ጸሎትን ማመልከቱ ይመስላል ።

ISIC

የእግረኛ ጦር እንዳስከተለ በሺ ወደሚቆጠሩት ክርስቲያኖች ሄዶ ይወጋቸው ዠመር ። እነሱም ወደ አለቆቻቸውና ወደ ዋናው ጦር ሠፈር በመሸሽ ፈንታ በሌላ መንገድ ወደ እንጾኪያ ተራራ ወጡ ። እስላሞቹ እየተከታተሉ ፲፪ ፈረሰኛ ገድለው ፲፭ ፈረስ ማረኩባቸው ። ከዚያ ጊዜው ስለመሸ እስላሞቹ ወደ ሠፈራቸው መጡ ። ይማ

ወዚር አዶሌና ወዚር ኑር ሌሎቹም በየሥፍራቸው ይጠባበቁ የነበሩት ክርስ ምና ጓደኞቹ የባሌን ጦር መውጋታቸውን ሲመለከቱ ከምሽጋቸው እየወጡ ክርስቲያኖቹን መውጋት ዠመሩ ። ጦርነቱንም የዠመረው ኤሚር ሁሴን ነው ።ከዚያ ጎይታ አላህ መጀን ፤ ገራድ ማታን ፤ ገራድ ሻሙን ፤ ተከታትለው ይዋጉ ዠመር ። በእስላሞቹና በክርስቲያኖቹ መከከል አንድ ወንዝ ነበረ ፈረሰኛ ሊያሻግር የሚች ለውንም ጉበዛዝቱ ክርስቲያኖች ይጠብቁት ስለነበረ እስላሞቹ በእነርሱ ላይ ገሥግሠው ወረዱባቸውና እየወጉ እስላም (ራስ እስላም ሰገድ) አለበት ድረስ አባረሩዋቸው ። ኤሚር ሁሴን ኤል ጋቱሪ ክርስቲያኖችን በወጋ ጊዜ ክርስቲያኖቹ ከበው ቋንዣውን መትተው ክፉኛ ከአቆሰሉት በኋላ ሸሽቶ ወደ ወገኖቹ መጣና ዳነ ።

እስላም ጦሩን እንደያዘ ይኸን ሁሉ ባየ ጊዜ ፈርቶ ወደ ኋላው ሊሲቱን አፈግፍጎ ድንኳኑን አስተክሎ እቅርብ አደረ ። እስላሞቹ ግን በዚያው በያዙት ሥፍራ አድረው የእንጾኪያ (የአይፈርስ) ጦርነት በዕለተ ዓርብ በረጅብ ፱፻፴፯ የሂጂራ ዓመት ተደረገ (1) ።

በማግሥቱ የቀ፲፬ቮርሃን ሲታይ እስላሞቹ ጸሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ፈረሶቻቸውን ወደ ጉን አስረው ከበቅሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ወደ እንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን አልፈው ደረሱ ። ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው ከትልልቅ የግንድ ርብርብ ላይ ነበር ። ይማም አህመድ "አቃጥሉ" ብሎ አዘዘና ተቃጠለ ። ከዚያ በታችኛው በኩል ትንሽ ተጓዙ እስላም ሊሲት ሄዶ እንደሆን አልታወቀም ፣ ወሬው በፍጹም ጠፋ ። እስላሞቹም አንድ ሜዳ ላይ ሆነው እስላም በየትኛው መንገድ ሄዶ ይሆን እያሉ እርስ በራሳቸው ሲነጋገሩ ባጠገባቸው ሁለት መንገድ አገኙ ። አንደኛው ብዙ የፈረስ ኮቴ አልፎበት ነበርና ይማም በየትኛው እንሂድ እያለ ሲያመነታ አዶሌና አብድ ኢን ናስር በዚህኛው እንሂድ ብለው ኮቴው በታየበት በቀኙ በኩል መድፉን ይዘው እንዲሄዱ አዘዛቸውና እርሱ ራሱ የኋላ ደጀን ሆኖ ጉዞው ተዠመረ ። ጥቂት እንደተጓዙ አንድ እስላም "እነዚያውና ክርስቲያኖቹ ከኋላ ሊወጉን ነው" ብሎ ጮኸ ይማም ከነወታደሩ ፊቱን አዙሮ የክርስቲያኖቹን ሰላዮች ያባርር ዠመር ። ክርስቲያኖቹም ገሥግሠው ወደ አንድ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ገቡ ። በዚያም እስላም ነበርና "ጦርህን አዘጋጅ እስላሞቹ እነዚሁና እኋላችን" አሉት ክርስቲያኖቹ ሁሉ ፈረሶቻቸውን ተነሥተው ጫኑ ። እስላሞቹም ገሥግሠው ጦርነቱን ዠመሩ ። ውጊያውንም የዠመረ በካሪ ቤን ዓሊ ይባላል ። እርሱም አንዱን የክርስቲያን ሹም በጦር ወግቶ ጣለው ። አቡበክር ቀጢንም አውራይ አቡንም አውራይ ኡመር ዲንም ......እንደዚሁ የገጠማቸውን እየወጉ ገደሉ ። ከዚያ ክርስቲያኖቹ

(1) ይሀ የሑጅራ ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ነው ።

ሸሽተው በዛፍ ወደተሸፈነው ተራራ መውጣት ጀመሩ ። እስላሞቹም እየገደሉ እየማረኩ ተከታተሉዋቸው ። ባጠገባቸውም ደርሰው ብዙ ፈጁዋቸው ። ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ እንደዚህ ቀን ክርስቲያን አልቆ አያውቅም ።

እስላሞ (ራስ እስላም ሰገድ) ከዚያ ሸሽቶ ወደ ሐድያ ሄደ ። እስላሞቹም ምሽት እስኪገላግላቸው ድረስ ሲያባርሩት ውለው ሳይሆንላቸው ቀርቶ ተመለሱ ። ይማም አህመድ በዚሁ በአይፈርስ ድንኳኑን አስተክሎ ሠፈረ ። በዚህ ቀን ከክርስ ቲያኖቹ ላይ የተማረከው ድንኳንና በቅሎ አይቆጠርም (ተቆጥሮ አያልቅም) ። እያ ዳንዱ እስከ ፴ ያገኝ አለ ...... ። የሬሳውና የሟቹ የምርኮኛው ብዛት ከልክ ያለፈ ነበር ። እያንዳንዱ እስላም እስከ ፤ ድረስ ማርኮአል ። ሌሊቱንም ሁሉ እስላሞቹ በዙሪያው አገር ያለውን ክርስቲያኑን ሲያሳድዱ አደሩ ። በዚያም ሌሊት ትልቅ ብርድ ተነሥቶ ብዙ እስላሞች ሞቱ ።

ወዚር አዶሌና አብድ ኢን ናስር ግንባር ቀደም ሆነው መድፉን ይዘው ሲጓዙ የይማምን ወደ ኋላ መመለስ ሰምተው ደንግጠው ስለነበረ አዶሌ "ጓዛችንንና መድፉን እመሬት ወርውረን ወደ ይማም በሩጫ ሄደን እንድረስ ብሎ ለአብድ ኢን ናስር ነገረው ። እርሱ ግን "አንተ ብትፈልግ ሂድ እኔ ግን መድፉን ትቼ አልሄድም ይማም እንደአዘዘው መድፉን ይዤ መጓዝ አለብኝ" ብሎ መለሰ ። የናስር ቀጥሮ አሳብ በታወቀ ጊዜ ሁሉም እውነቱን ነው ብለው ባንድነት እየተጓዙ ይማም ወዳለ በት ሥፍራ ተጠግተው ሠፈሩ ። ይማም ከደረገው ጦርነት ሸሽተው በጫካ የነበ ሩት ክርስቲያኖች እስላሞች በርዷቸው እሳቱን ሲሞቁ በሩቅ ሲያዩ ጓደኞቻቸው መስለዋቸው ሊሞቁ መጡ ። እስላሞቹም ወዲያው ድንገት ይዘው ፳፻ውንም ፈጁ ዋቸው ...... ። በማግስቱ ወዚር አዶሌና አብድ ኢን ናስር ጉዞአቸውን ቀጥለው በአሥር (ሰዓት) በይማም ደረሱበትና እርስ በርሳቸው ሰላምታ ሲሰጣጡ ባገኙትም ድል እምላካቸውን ሲያመሰግኑ ቆዩ ።

ከዚያ ይማም ፋራቃሃም ዲንን አስጠራና ፴ ፈረሰኛ ሰጥቶ ክርስቲያኖችን እያባ ረርህ ግደል ብሎ ወደ መጅራህ ሰደደው ..... ወዚር አዶሌንም "እኋላ ሆነህ ባለ ፈው ጦርነትና ምርኮ አልተካፈልህምና አገሩን ዝረፍ ከብቱንም ንዳው" ብሎ ላከ ው እርሱም በያለበት ፈረሰኞቹን እነድል ሰገድን እነተክላይን ..... ወደ ሻርካህ በግራና በቀኝ እየላከ ...... አገሩን አስመታ (1) ።

በሻርካህ ከዚህ ቀደም ስሙ የተነሳው ቢትወደድ በድላይ ነበር ። እርሱም በመጀመሪያ እንደተጻፈው ከአዝማች ደገልሃን ጋር ወደ አንጾኪያ ከመጣ በኋላ ደገልሃን ወደ ንጉሡ ተመልሶ በርሱ ፈንታ እስላሞ የተሾመ ጊዜ በበላዬ ለምን ተሾመ ብሎ ተቀይሞ "ንጉሡ ከኔ በላይ ሾሞሃልና እንግዲህ ለንጉሡ ክብር ተዋጋ" ብሎ ወደ ሻርካህ መጥቶ ተቀምጦ ነበርና አሁን እስላሞቹ ወደ አገሩ መግባታቸ ውን ስለሰማ ለጦርነት ተሰልፎ ይጠባበቃቸው ጀመር ። የመጡትም እስላሞች ግማሾቹ ተመልሰን ለወዚር አዶሌ እንንገርና ረዳት ጨምረን እንዋጋው ሲሉ የቀ ሩት አሁኑኑ እንዋጋው ብለው ቆረጡና ..... ጦርነቱን ጀመሩ ። አለቃው ካሲታ

(1) ሻርካህ የሚለው ምናልባት በአሩሲ ውስጥ ያለውን የሺርካ ወረዳ ይሆናል ።

የእግረኛው ጦር ከእግረኛው ጋር በየግንባሩ ገጥሞ ይፋጅ ገመር ። ተክላይ (አባቱ አበሻ) . . . . . አንዱን የክርስቲያን አለቃ ፥ አብዝድ አንዱን የንጉሥ የልፍኝ አሽ ከር የነበረውን ፈረሰኛ እየመታ ባሉ ። የሴፍ የሚባለውም በቢትወደድ በድላይ ላይ ተወርውሮ ሊማርከው ሲል ቢትወደዱ ነገሩ ቀርጥ መሆኑን ሲረዳ ከፈረሱ ወረ ደና በግሩ ሮጦ አንድ ወንዝ ተሻግሮ አመለጠ ። የሴፍም ፈረሱን ብቻ ማረከ ። የቀ ሩት ክርስቲያኖችም . . . : . የአለቃቸውን ሽሽት የፈረሱን መማረክ ሲያዩ ሽሽታ ቸውን ያዙ . . . . . እስላሞቹም የማረኩትን እንደያዙ ጀንባህ ወሰን ላይ ከመዚር አዶሌ ጋር ተገናኙ ። የማረኩዋቸውንም ሹማምንት አሳዩትና . . . . . ታላቅ ደስታ አደረጉ ። በኋላም ወደ ይማም ሄደው ተገናኙ ። የተማረኩትንም ሹማ ምንት እይማም ፊት አቀረቡዋቸውና ማዕርጋቸውን ጠየቃቸው ። ከእነሱም አንዱ የንጉሡ የልፍኝ አሽከሮች አለቃ "እኔ በሁለት መቶ ጥሩ የወቄት ወርቅ እገዛለሁ" አለ ። ጓደኛውም "እኔም በመቶ ወቄት እገዛለሁ" ብሎ ተናገረ ። ይማም ግን "የናንተ ወርቅ አያስፈልገንም" ብሎ ሁለቱንም አስገደላቸው (1) ።

እስላሞቹ በገርንባህ ፮ ቀን ባደሩበት ጊዜ በሀበሻ አገር (በዚህ ጦርነት) የሞቱ ትን ሼክ ዛማካህ የሸዋ ተወላጅና ኡስማን የሚባሉትን ሁለት የተከበሩ እስላሞች ቀበሩ ። ከዚያ በይማም ትእዛዝ ወዚር አዶሌና ወዚር ኑር ወደ ሻርቃህ ሄደው የክር ስቲያኖቹን ሚስቶችና ልጆች ይዘው ብዙም የምርኮ ዕቃና ልዩ ልዩ ልብስ ይልቁ ንም ቍጥሩ የበዛ ወርቅ አግኝተው ወሰዱ ። ጦርነቱ ከተዠመረ አንስቶ ብዙ ወርቅ በምርኮ የተገኘበት ይህ ያሁኑ ጦርነት ነው ።» ሲል የዓረቡ ጸሐፊ ራሱ የነበ ረበትን የአይፈርስን ውጊያ በዚህ ዓይነት ይዘረዝራል ።

የኛ ታሪክ ነገሥት በሦስት መስመር የቀረጠውን ይኸኛው ሥፍራና ጊዜ እየ ለየ የተዋጊና የአዋጊ ስም እየጠቀሰ ታሪኩን በዝርዝር ባይጽፈው ኖሮ በዚህ በአ ይፈርስ ላገራቸውና ለንጉሥ ነገሥታቸው ሕይወታቸውን የሠዉት ታላላቅ የጦር አለቆች ስምና ይልቁንም የጦርነቱ ታሪክ እንደተቀበረ ሊቀር ይችል ነበር ። ስለዚህ ምንም ለኛ ሲል ባያደርገው ይኸን የጠላት ጸሐፊ ማመስገን የተገባ ነው ።

እንደ እውነቱ እንደሆነ ምንም እንኳን በራስ እስላም ሰገድ ውስጥ ቢሆን አቤት (አቤል ?) ተብሎ በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ የተወሳው ዝግና ሹም የባሌን ጦር ይዞ በእንጾኪያ የተዋጋው ከፍተኛ ስለሆነ የእንጾኪያና የአይፈርስ ጦርነት ሊባል ይገባዋል ። ዓረብ ፋቂህ በጽሑፉ ብዙ ጊዜ የባሌን ጦር ዠግንነት ይገልጻል ። ይኸም በዚህ በአይፈርስ ጦርነት ብቻ ሳይሆን ባለፈው ግራኝ በባሌ ከነሽንቁር ጋር የተዋጋ ጊዜ « የባሌ ሕዝብ ሰይጣን ነው ምን ይሻላል» ብሎ እስኪቸገር ድረስ ከፊ ትና ከኋላ እያደፈጡ የወጉት ትዝ ይለናል ። የባሌ ሕዝብ ሲል እንደዛሬ ከሸዋ ከበ ጌምድር ፥ ከጐጃም ሄዶ እንደወርዋሪ የተተከለውን የአማራ ሕዝብ ይሁን ወይም የአገር ተወላጁን ይሁን ወይም ሁለቱም ተደባልቀው ያሉበትን ይሁን አይታወ ቅም ። ነገር ግን ዛሬ የዚያ አገር ተወላጅ የሆኑት ጋሎች በዚያን ሰዓት በብዛት

(1) ይህ የልፍኝ አሽከሮች አለቃ አብዲናጎ ይሆን ? አልቫሬዝ ምዕ. 107 ምዕ. 117

ባሌን ወርረው ስላልገቡበት በዚህ ጊዜ በባሌ ያለው የሸዋና የአማራ እንደዚሁም ቀደም ብሎ የገባ የጋላ ሕዝብ ጭምር ያለበት ጦር ይሆናል ።

እስላሞቹ ወደ እያፈርስ ሲጓዙ አንድ ትልቅ ወንዝ እንዳገኙ በዚያም ሁለት መሻገሪያ አግኝተው ከሁለቱም አንዱን ብዙ ሰው የሚያውቀው ሌላውን ጥቂቶች ብቻ ያውቁት እንደነበረ እስላሞቹም ብዙ ሰው በማያውቀውና ባንድ ውስጥ አዋቂ የእስላም መሪነት ባልተያዘው በላይኛው መንገድ እንደልባቸው አልፈው ሌሊቱን አድረው በማግሥቱ ጦርነቱን መገርመራቸውን በአለፈው ዓረብ ፋቂህ የገለጸልን አተራረክ እውነት እንደሆነ በክርስቲያኖቹ ዘንድ አሁንም ያው የተለመደ የቸልታ ሥራ በዚህ ጦርነት ላይ ሲደርስ ይታያል ።

ያገሩን ፡ የመንገዱን ፡ የወንዙን ሁኔታ ከእስላሞቹ ይበልጥ ክርስቲያኖቹ በዝርዝር የገዛ አገራቸውን ማወቃቸው የታወቀ ሲሆን የታችኛውን አስጠብቀው የላይኛውን ያለጠባቂ የተዉበት ምክንያት ሊገባን አይችልም ፤ ጦርነቱን ራሳቸው ፈልገውት እንደሆነ ሁለቱንም ሳይዘጉ እንዲያውም ራሳቸው ወንዙን ተሻግረው አጥቂ ሆነው ሊዋጉ ይችሉ ነበር ። ያለዚያ መከላከል እንደሆነ አሳባቸው መተላለፊያውን በር ሁሉ ማስጠበቅ ነበረባቸው ። የዚያን ጊዜ ጦርነት ደግሞ አብዛኛው በመትረየስና በጥይት ሳይሆን ውጊያው ተደበላልቆ በጦርና በጐራዴ በሰይፍና በቀስት በትር በጋሻ ምክት በትንንቅ ስለሆን ምሽግና ዲብ ይዤ ጠላቴን ልጠብቀው የሚያሰኝ አልነበረም ። ለጦርነት የዚያን ጊዜ የሚመረጠው ሥፍራ ለፈረሰኛ የሚመች ሜዳና ለእግረኛ ጦር የሚመቸው ነው ። ቀስተኛው ግን እንደልቡ ተደብቆ ጠላቱን የትም ሆኖ ለመጉዳት ጫካን ይመርጣል ። ተራራማና የሸለቆ ሠፈርም ለናዳ ይመቻል ።

የሆነ ሆኖ ሁለቱንም በር በሙሉ አስጠብቀው ቢሆን ድሉ እንኳን ቢያጠራጥር የጠላታቸውን ጦር የበለጠ ሊጐዱበት በቻሉ ነበር ። ይቺን ፪ኛዋን መንገድ ግራኝና ሰዎቹ እያውቋትም በሚለው እምነት ጐን ግራኝ በግድም በውድም ምርኮኛም ቢሆን ውስጠ አወቅ መሪ አያጣም ብሎ መጠርጠር እንደምን ቀረ ? ።

ከዚህ ጋር የራስ ደገልሃን በእጅ አዙር መመለስና የራስ እስላም ሰገድ በበላይ መሾም የቢትወደድ በድላይን መቀየም ስላስከተለ የዚህ ሁሉ ሁኔታ የክርስቲያኖቹን የጦር ግንባር እንደሚያላላው አይጠረጠርም ። ከንጉሡ ዘንድ ወደ አንጾኪያ ለውጊያ የመጣው ቢትወደድ (ብሕት ወደድ) በድላይ የበላዩ ደገልሃን ከተመለሰ እኔ በእርሱ እግር ተተክቼ ጠቅላይ ጦር አዝማች እሆናለሁ ሲል በንጉሡ ዘንድ ደግሞ በድላይ ለዚህ ደረጃና መሪነት የማይመጥን በመሆኑ ይሁን ወይም ስሙ እንደሚያመለክተን ካዬ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር የተዋጋው የመሐመድ በድላይ ተወላጅ እንደሆነ የጥንት ወገኖቹን ከልብ ሊወጋ አይችልም ተብሎ በሙሉ ባለመታመን ይሁን በደገልሃን ሥፍራ በርሱ ደረጃ የሚገኘውን በስምም በማዕርግም የሚበልጠውን ራስ እስላም ሰገድን ሾመው ሲልኩ ራስ እስላም ሰገድ በደገልሃን ለሞት መለወጡ ቅር ሊያሰኘው ይችላል ። የሆነ ሆኖ ራስ እስላም ሰገድ እይፈርስ ሲደርስ ቢትወደድ በድላይ ተቀይሞ "በል . . . . . የበላይነት ተሾመሃልና አን

ተው ተዋጋ" ብሎ ጥሎት ወደ ሻርካህ ሲሄድ ይኸን በመሳሰለው ባል ተሳካና በእል ተቀናበረ ሁኔታ ብልሁና ጉበዙ ግራኝ አህመድ በመጠቀም የሁለቱን እለቆች የጦር ሠራዊት በየተራ ለየብቻ እየመታ አሸነፋቸው ማለት ነው ።

ይኸን የመሳሰለ የአለቆች አለመስማማትና መለያየት ጠላትን ሲጠቅም የኖረ ወደፊትም የሚኖር መሆኑ ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ ቢትወደድ በድላይ ጠቅላይ አዝማችነትን ያጣው ባለመታመን እንደሆነ እርሱ ያውም የራስ እስላም ሰገድ ጦር ከፈረሰ በኋላ ተስፋ ሳይቆርጥ በመዋጋት ታማኝነቱን አረጋግጧል ። ነገር ግን ለየ ብቻ በመዋጋት ፈንታ ሁለቱ ባንድነት ተዋግተው ቢሆን የበለጠ ፍሬ ባሳዩ ። ምና ልባት ሊያሸንፋም በቻሉ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲጣላ መላም ዘዴም ይጠ ፋል ፤ መለያየትም ይከተላል ። በመለያየትም ማናቸውም ቤት እንደማይቆም መጽ ሐፍ የተናገረው ትክክል ነው ።

የሆነ ሆኖ ከዚህ ሁሉ ይበልጥ ለግራኝ አህመድ በእቤት የተመራውን የእን ጾኪያን በራስ እስላም ሰገድ አዝማችነት የወደቀውን የእይፈርስን የጦርነት ድል ያረጋገጡለት ከዓረብ አገር ገዝቶ ያመጣቸው አዳዲስ መድፎች ናቸው ። በአንጾ ኪያ ጦርነት የባሌ ተዋጊዎች እስላሞቹን ከበው በግራና በቀኝ እያዋከቡ ብዙ ጉዳት ባደረጉባቸው ጊዜ ግራኝ በዚህ ዓይነት እየተዋጋችሁ ታልቃላችሁ ብሎ ሹማምንቱን እነገራድ ማታንን ተቆጥቶ አቁሞ የመድፍ ተኩስ የሚያውቀውን ሰይድ ቤን ሳባን መድፉን በክርስቲያኖቹ ላይ እነጣጥሮ እንዲተኩስ አዞት እስተካ ክሎ ሲተኩስባቸው በክርስቲያኖቹ መካከል የነበረውን ምናልባት እንደተገን ያደ ረጉትን ወይራ እሁለት ሲጉምደው ይኸን የመሰለው በክርስቲያኖቹ ዘንድ የሌለ ብቻ ሳይሆን ያልታወቀው አዲስ መሣሪያ አጯጯሁና አመታቱ የዠግናን ወኔ ገድሎ የወታደርን የተዋጊነት መንፈስ አብርዶ ሽሽትን ፍርሃትን እንደሚያስከ ትል የታወቀ ነው ። በዚህ ምክንያት ራሱ የዓረቡ ጸሐፊ ግራኝ የያዘው መድፍ የወ ይራውን ግንድ ከሁለት ሲጉምደው ተዋጊዎቹ ተነባብረው ወደቁ ያለውን እናስታ ውሳለን ።

ግራኝ በጦርነቱ ሰዓት አንተ መድፉን መዠመሪያ ተኩስባቸው ከዚያ ቀጥሎ እኛ እንወጋቸዋለን ማለቱ አንተ በመድፍ አስደንግጠህ ሐሞታቸውን ካፈሰስኸው በኋላ እኛ የደነገጡትን እያባረርን በጉራዴና በጦር እንጨርሳቸዋለን ማለቱ ስለ ዚህ ነው ። ሁኔታው ሳይኮሎዠ የተደገፈ ታላቅ የአጥቂነት ዘዴ ነው ። ይኸን ንም ዘዴ ከራስ ነቢያት የተዋጋ ጊዜ ባንዲት ጥይትና ጠመንጃ በኡስማን ተኳሽነት የተጠቀመውን መልሰን በዚህ ጊዜ እናስታውሳለን ።

ምናልባት የኛዎቹ ወታደሮች እስከዚህ ጊዜ ድረስ ወሬውን እንኳን ቢሰሙ ከዚያ በፊት የመድፍን በትሩንም ባይናቸው ዓይተው ድምጹንም ሰምተው እያው ቁም ይሆናል ። በእጃቸው የሌለው ይህ መድፍ እጠገባቸው ያለውን ወይራ ከሁ ለት ሲጉምደው ሲያዩ ምንም የልብ ዠግንነት ቢኖራቸው እኛን ቢያገኝን ኖሮ ይኸው ነው በሚል ግምት መሸበርና ተስፋ መቁረጥ እንደሚመጣባቸው የታወቀ ነው ። በዚህ ድንጋጤና ሽብር መካከል በፕላን የታዘዘ ጦር ተንደርድሮ ሲገጥማ

ቸውም ከመሸሽና ከመሸነፍ ዘልለው መመከቱ ያዳግታቸዋል ።

በ፲፱፻፳፯-፳፰ ዓ.ም. በማይጨው የኢትዮጵያን የጦር ሠራዊት አሸንፎ የበታተነው የኢጣሊያኖች ጥብቅ ተዋጊነታቸውም ዠግንነታቸውም የጦር መላ አዋቂነታቸውም አልነበረም ። ይህ ቢሆን ኖሮ የዓድዋውንም ድል ባላጡ ነበር ። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን እጅ የሌለው በነርሱ ዘንድ የረከሰው የአየር ኃይልና የቦምብ በትር ከዚያ ደግሞ የበለጠ በዓለም ሕግ የተከለከለው የጋዝ መርዝ ነው ። ለብዙ ዘመን እዋጋለሁ ጠላቴንም እንዳባቶቼ አሸንፋለሁ ብሎ የተማመነው ወታደር በዚህ የአየር ኃይልና መርዝ እየተመታ ቅጥ እጥቶ መበታተን ግዴታ ሆነበት ። የግራኝ መድፍም በዚያ ከጦርና ከጐራዴ ከቀስት በቀር ለማያውቅ ጅምላ ወታደር ያው የቦምብና የጋዝ መርዝ ያህል የሚቆጠር ስለሆነ ከሽምብራ ኵሬው ጦርነት ይልቅ ይህ ያሁኑ የአይፈርሱ ጦርነት መሸነፍ ሊያስገርም አይችልም ።

በዚህም ላይ ጦርጦራው መሪ ግራኝ አህመድ በውጊያው ሰዓት ወዲያና ወዲህ እያለ የውጊያውን እርምጃ ራሱ በቅርብ እየተከታተለ ምክርና የጦር መላ ከየአለቆቹ እየተቀበለ ለየአለቆቹ የራሱን እያደለ ተዋጊውን በንግግር እያነቃቃ ሲያበረታ ልግም ራሱ እየተዋጋ ጦሩን በማዋጋቱ በማይመች ቦታ ሆኖ ይዋጋ የነበረውን አማቹን ማታንን በቁጣና በግልምጫ ከእጉሉ ቦታ አስነቅሎ ወደሌላ ቦታ እንዲዛወር ማድረጉ የጦርነቱን አመራር ራሱ በእንዴት ያለ ዘዴና ብርታት እንደሚቆጣጠር በግልጽ ይታያል ።

ISIC

ስለዚህ የርሱ በየጦሩ ግንባር መገኘት ጥብቅ ተዋጊነቱ ብልህ መሪነቱ ዘዴኛነቱ ፤ በእጁ ያለው አዳዲስ መሣሪያ ፤ የንጉሡ በጦር ግንባር ተገኝቶ እንደርሱ አለመምራት ፤ የሹማምንቶቻቸው በአሳብ መነጣጠል መንገድ አለማስጠበቃቸው ዘመናዊ መሣሪያ ማጣታቸው ተባብሮ ራሳቸውን አስጠቅቶ ጠላታቸውን ግን ሁል ጊዜ ከድል ወደ ድል እንዲራመድ ረድቶታል ማለት ነው ።

ከድሉ በኋላ የሆነውን ራሱ ዓረብ ፋቂህ በራሱ አነጋገር ስለዘረዘረው ሁለተኛ ሐተታ መስጠት የአንባቢን ጊዜ በከንቱ መውሰድ ነው ። ከአይፈርስ ድል በኋላ አሸናፊው የእስላም ጦር በየመስመሩ እየዞረ ከጦሩ ቦታ የሚሸሸውንም በባላገር ያለውንም በጦርና በሰይፍ እየመደመደ መፍጀትና የቀረውንም ማስለም ሆነ ። በዚህም ጊዜ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተዘርፈው ተቃጠሉ ። ከዚህም ውስጥ ሥራው ፲፩ ዓመት የፈጀ በደዋሮ ግዛት በተለይ አንዱራህ በሚባለው ቦታ ራስ ወሰን ሰገድ ያሠራት አንድ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረች እስላሞቹ ወደ ውስጧ ገብተው ሥራዋንና በውስጧ ያለውን ሥዕል የከበረውን ንዋየ ቅድሳትና ከግሪክ አገር የመጡትን ታላላቅ ሥጋጃዎች እያዩ ካደነቁ በኋላ ሀብቷን ዘርፈው እንዳቃጠሏት ዓረብ ፋቂህ በተጨማሪ ይገልጻል (1) ።

ይኸን ከመሰለው ጥቃት ዓፄ ልብነ ድንግል ሊድኑ ይችሉ የነበረው ከዚህ በፊት እንዳልነው ቀደም ብለው ዘመናዊ የጦር መሣሪያና ተዋጊ ወታደር ቢያደ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 190 - 195

ደብ ብለው ገሰገሱ ፲፭ ዓ. ም. በመዠመሪያ ደገልሃንን ድል አድርጎ ያባ
ራጁ አለዚያም ግራኝ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. በመዠመሪያ ደገልሃንን ድል አድርጎ ያባ
ረረ ጊዜ እነዚህን ሁሉ አሁን በየተራ እየመጡ የሚያልቁትን የጦር አለቆች እንዳስ
ከተሉ በዚያው ዓመት ግራኝ እንዳሁኑ ሳይደረጅ ከነሱልጣን አቡበከር ከነኡመር
ዲን በተጣላበት ጊዜ አዳል ድረስ ሄደው ዓፄ ዓምደ ጽዮን በወሰደው እርምጃ መሠ
ረት አገሩን ወርረው ጦሩን በታትነው አደገኞቹን የጦር አለቆች ማርከው ተመል
ሰው ቢሆን ምናልባት ይህ ወረራ በጊዜአቸው ደርሶ ይኸን የመሰለ ውርደትና እል
ቂትን ባላመጣ ። ይኸንንም በሚያደርጉበት ሰዓት ጦርነት የሰለቻቸው ኡሚሮችና
በተለይም የግራኝ ጠበኛ የነበረው ሱልጣን አቡበከርና ወንድሙ ኡመር ዲን ምና
ልባት ከርሱ ተለይተው ከርሳቸው ጋር በተስማሙ ነበር ።

ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳስታወስነው በመዠመሪያ ላይ ገና ስሙ ላልታወቀ
ይማም አህመድ ተብሎ ለተነሣ የሱልጣንነት ደረጃ እንኳ ለሌለው ንጉሠ ነገሥቱ
አዝማች ሆነው ጦር ይዘው መሄዱ ያን ጊዜ ውርደት መስሎ ይታያል ። ወደፊት
ይኸን ያደርጋል ብሎ በቅድሚያ ለመገመትም ችግር መሆኑ አይጠረጠርም ። የግ
ራኝን የወደፊት ዓላማውንና አደገኛነቱንም ከጦር ድርጅቱ ጋር ሐረር ሰላይ ልኮ
መረጃ መሰብሰቡና በኋላም መድኀኒቱን ለመፈለግ የቤተ መንግሥቱ የስለላ
ኃይል ደካማ መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

በዚህ ዓይነት ጠ... ከመዠመሪያው ላይ የመናቅ ስሕተት ካፄ ልብነ ድን
ግል በፊትም በኋላም በዓለምና በኢትዮጵያ ጠፍቶ ስለማያውቅ ሁልጊዜ ተናቂ
ዎቹ በመናቃቸው ሲጠቀሙበት ናቂዎቹም በትዕቢታቸውና በንቀታቸው ሲዋረ
ዱበት ኖረዋል ። ወደፊትም ይኖራሉ ። እንደዚሁም ጠላት ከደጅ እስኪመጣ ድረስ
በመጠበቅና በመከፋፈል በኩል ያለው የዓለም ስሕተት በታሪክ ውስጥ ሁል ጊዜ
ተደጋግሞ እንደታየና ዛሬም የሚታይ ነው ።

ጥንት ሮማውያን በ፩፻ ፶፮ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ዠምረው ካርታ
ዥን (ቱኒዝን) ሲራኩዛን (ሲሲልን) ኢስፓኝን ጋልያን (ፈረንሳዊን) ሲወጉ የቀሩት
አገሮች ብሪታንያ ማውሪታንያ (ማሮክ) ግብፅ ግሪክ እንጾኪያ እደጃቸው ድረስ እየ
መጡ የመንግሥታቸውን አቅዋም በየተራ እየመቱ ሲያፈርሱና የራሳቸው ተገዥ
እስኪያደርጓቸው ድረስ ዝም ብለው ወሬውን በየአገራቸው እየሰሙ ተቀምጠው
ነበር ። ሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ እ.አ.ቈጥር ፲፱፻፴፱ - ፲፱፻፵፭ ዓ.ም. ሂትለር አትሪሽን፣
ፖሎኝን ፣ ቼኮስሎቫኪያን ሲወር በዚያው ወረራውን በዠመረበት ወቅት እንግሊ
ዝና ፈረንሳዊ ከነዚያ በቅድሚያ ከተወጉት አገሮች ተባብረው አልመከቱም ። ፈረ
ንሳዊም ሲወረር እንግሊዝ በተለይም መስኮብና አሜሪካ ወደ ጦርነቱ በቶሎ ለመ
ግባት አልቻኰሉም ። መስኮብም ከገባ በኋላ እንግሊዝና አሜሪካ ጀርመን ላይ
የጦር ግንባር በቶሎ አልከፈቱም ። ቀደም ብሎም ጀርመን ፈረንሳይን ፣ ፖሎኝን
ሲወር በበኩሉ ናዚስምና ካፒታሊስም ተዋግቶ እንዲዋደቅለት መስኮብም ከመጠ
በቅ ጋር እንዲያውም ፖሎኝ ሲወድቅ ከአሸናፊው ከጀርመን ጋር ሆኖ የመሬት
ምርኮ ተቀራምቷል ። መቸም የመንግሥት መሪዎች ሁሉ ያገራቸውንና የራሳቸ
ውን ቀጥተኛ ጥቅም እንጂ የሕሊና መንገድ የተባለውን አያውቁትም ።

ይኽ የመከፋፈል ሁኔታ ለሂትለር በአውሮፓ ላይ ወረራውን ካቃናለት በኋላ
ከሩቁ ከአሜሪካ በቀር ሁሉንም ራሱ እየወጋ ስለቀሰቀሳቸው በመጨረሻ በግዴታ
ተባብረው እንዲወጉትና እንዲጥሉት ራሱ ጭምር መጥፊያውን እንደአዘጋጀ ይታ
ያል ። ስሕተት መልኩንና ጊዜውን ይለዋውጣል እንጂ ተሸናፊንም አሸናፊንም
አይምርም ። የስሕተትም ስሕተትነቱ የሚታወቀው በመጨረሻ በዕረፍትና በሰ
ላም ዘመን ሁኔታው በተመዛዘነ ጊዜ ነው ።

ፈረንሳዊና እንግሊዝ ሂትለር በአትረሽ ወረራ ይቆም እንደመሰላቸው ዓፄ
ልብነ ድንግልም ግራኝ አህመድ የቀድሞዎቹ የአዳል ባላባቶች እንደሚያደርጉት
አንድ ጊዜ መጥቶ ከአዛዥ ደገልሃን የተዋጋ ጊዜ ያገኘውን ዘርፎ ወዳገሩ የሚመ
ለስ መስሏቸው ነበር እንጂ ተመልሶ እኔን በሽምብራ ኩሬ ላይ ተዋግቶ ያሸንፈኛል
ብለው በፍጹም አልጠረጠሩም ። ለዚህም ማስረጃው ወደ ሽምብራ ኩሬ ጦርነት
ሲመጡ እስላሞቹ እንዳያመልጧችሁ ሁሉንም ያዟቸው የሚል ትእዛዝ ለጦር አለ
ቆቻቸው አስተላልፈው እንደነበር ምርኮኛም የሚታሠርበት የገመድ መሣሪያ
በብዙ ተይዞ እንደነበር ዓረብ ፋቂህ ያረጋገጠው ትዝ ይለናል (1) ። ነገር ግን ያልገ
መቱት በራሳቸው ላይ ተመልሶ ሲደርስና ሲሸሹ በሸሹበትና በተሰደዱበት ሁሉ
መደነቅና መገረም ከአእምሮአቸው ሊጠፋ አይችልም ። ባለፈውም የጠፋውን
ጊዜ ተመልሶ እንደማይገኝ ሲያመዛዝኑት ቁጭቱ እየተባባሰባቸው መሄድ አለ
በት ።

ISIC

ምዕራፍ ፵፮

የዛሬ ጦርነት - የራስ እስላም ለገድና የትግሬ መኳንንት ተከለ ኢየሱስ ሞት
(ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) — ግራኝ አህመድ ለዓፄ ልብነ ድንግል የጻፈው
ደብዳቤ ።

የግራኝ አህመድ መንግሥት ከርሱ ጋር ያለው ከዓረብ አገር ተገዝቶ የመጣው አዳዲስ
መሣሪያና ይልቁንም መድፉ ፤ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባዔ ልብነ ድንግል
በጦር አለቆቻቸውና በወታደሩ ላይ መሸነፍን ስላደረሰ በዚህ ዘመን በነበረው በነ
ጋዴው ፤ በገበሬውም ፤ በካህኑም ፤ በመነኩሴውም ፤ በትልቁም ፤ በትንሹም ላይ
ትልቅ መከራና ፍዳ አውርዶበታል ። የጦር አለቆች በየጦር ግንባር እየተጋፈጡ
ሲሞቱ ከነዚሁ ውስጥ የሚሞተው ተማርኮ የሚገደለው እንደ ባሪያ ወደ ዓረብ አገር
የሚሸጠው ለየአውራጃው ሱልጣን እንደ ዕቃ ተቆጥሮ መታየ የሚቀርበው ብዙ
ነው ። መኳንንቱና ሹማምንቱ ተሸንፈው በሞቱ ፤ በተማረኩ ቍጥር የሚወደ
ቸው ሚስቶቻቸው በእስላሞቹ እጅ ይወድቃሉ ። የጨከነውና ያልወደደው የእስ
ላም አለቃ ተማራኪዎቹን የክርስቲያን ሚስቶች ለእስላሚቱ ሚስቱ ገረድና ሬዋ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 116

አድርጎ ይሰጣቸዋል ። መልኳ አምሮት ደስ ያሰኘችው እንደሆነ እስልም እቁባት ያደርጋታል ። ክርስቲያኒቱም ወይዘሮ በተማረከችበት ጊዜ የማትፈቅደውን ሃይማኖት በግድ መያዝ የማትወደውን የእስላም ሹም ባልና ጌታ ለማድረግ ትገደዳለች።

ይኸም በማናቸውም የጦርነት ጊዜ መሸነፍ የሚወልደው ጉዳትና መከራ ስለሆነ ምንም ማድረግ አይቻልም ። ባጭሩ በዚያን ሰዓት በምርኮ የሚገኙ ሚስት ፡ ገረድ ፡ አሽከር ልጅ እንደከብት ፡ እንደሸቀጥ ተቆጥረው እስላሞቹ የሚወዱትን ለራሳቸው እያስቀሩ የቀረውን ይገበያዩበታል ። ክርስቲያኑ የጦር አለቃ በተማረከ ጊዜ ማራኪው የእስላም አለቃ ወይም ራሱ ግራኝ ቢጨክን ይገድለዋል ። ወይም ወደ ዓረብ አገር ለመጋረያ ለውጥ አድርጎ ይልከዋል ። አለዚያ አሥር ወራ ነጋሪ መንገድ መሪ ያደርገዋል ። አንዳንዱን ደግሞ እንደ በቅሎና እንደ ፈረስ ዋጋ ውጣ ውረድ ተብሎ ከዘመዶቹ እየተከራከረ ብዙ ወቄት ወርቅ እየተቀበለ ይለቀዋል ። ለጊዜው ወርቅ ከፍሎ የተለቀቀው በሌላ ጊዜ ተማርኮ ሊታሠር ወይም ሊሞት ስለሚችል በማናቸውም ረገድ ሁል ጊዜ የግራኝ ጥቅም እንደተጠበቀ ነው ። ባሁኑ ጊዜ የግራኝ አህመድ አነሣሥ ያለፈን ሁሉ በቀል ለመመለስ ኢትዮጵያንም ለመግዛት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ክርስቲያንነት አጥፍቶ እስልምናን ለመተካት በኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥት ፈንታ እስላማዊ መንግሥት ለማቆም ነው ።

ስለዚህ ተሸንፎም የተማረከውን ተስፋ ቆርጦ የገባውን ክርስቲያን ሁሉ እስላም እንዲሆን ይጠይቀዋል ። እምቢ ሲል ያስገድለዋል ። እሺ ብሎ የሰለመውን ትናንሽ ሹመት በመስጠት ምርኮኛ ሚስቱንና ልጁን በመመለስ ትንሽ እስተያየት ያደርግለታል ።

በተረፈ በግራኝና በጦር አለቆቹ ፊት የተገኘ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ያለው ንዋየ ቅድሳት የቤተ ክርስቲያኑ ሀብት ሙልጭ ብሎ በቅድሚያ ከወጣ በኋላ ፈጽሞ ይቃጠልና አመድ ይሆናል ። ይኸም ክርስቲያኖቹ ተሰብስበው የሚጸልዩበት የሚገናኙበት የሚመኩበት ቤተ ክርስቲያንና ገዳም በፊታቸው ጨርሶ ሲጠፋ ሕዝቡን ወደ እስላም ሃይማኖት ለመመለስ ይቀናል ተብሎ ነው ። ነገር ግን ወደፊት በዝርዝር እንደምናየው ለቤተ ክርስቲያናቸው ቀናዕያን የሆኑት መነኩሳትና ካህናት እንኳን ሃይማኖታቸውን ሊለውጡ ገዳማቸው ሲቃጠል በነበልባሉ ውስጥ እየገቡ በመቃጠል የሃይማኖታቸውን ጽናት አሳይተዋል ።

እስላሞቹም በደረሱበት አውራጃና ወረዳ ቀበሌና መንደር ሁሉ እየገቡ መጋረያ የያዘውን እየገደሉ የቀረውንም ነጋዴና ገበሬ የሆነውን በክርስቲያንነቱ ብቻ ሲፈጁት ሲዘርፉት ሲያምሱት ግራኝ ያልደረሰባቸው አውራጃዎች ባለፈው ተስፋ ሳይቆርጡ ሁል ጊዜ ለጦርነት ይዘጋጃሉ ። ከዚህ ቀደም የተዋጉትም ያልተዋጉትም የክርስቲያን የጦር አለቆች ከንጉሣቸው እየታዘዙ የራሳቸውም ቁጭትና እልህ እየያዛቸው የወገንም ጥቃትና በደል እየተሰማቸው በዚህ ምዕራፍ ራስ እስላም ሰገድና ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ተዋግተው ሲሞቱ ወደፊት በሚቀጥሉት ምዕራፎች እነራስ ወሰን ሰገድ ፤ እነ ዓምደ ሚካኤል (የጸሐፌ ላም ሮቤል ልጅ) ሌሎችም ብዙ መኳንንትና የጦር አለቆች የሚያደርጉትን ውጊያና ትግል ወደፊት እንመለከታለን።

ግራኝ ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስንና ራስ ወሰን ሰገድንም ከአሸነፈ ወዲህ ሸዋን አልፎ አማራ ሳይንት ፤ በጌምድር አንጎት ትግሬ ከዘለቀም ወዲህ ክር ስቲያኖቹ የጦር አለቆችና የየአውራጃ ገዥዎች ባለፈው በክርስቲያኖች ላይ የደረ ሰው ድል መሆን በግራኝም እጅ ያለው በእነርሱም እጅ የሌለው የመድፍ መሣሪያ ተስፋ ሳያስቆርጣቸው ያለዕረፍት እየገጠሙ ስለሀገራቸው ስለንጉሣቸው ፤ ስለሃይ ማኖታቸውና ስለክብራቸው ጠንክረው እየተዋጉ የእስላሞቹን ጦር የመለሱበት አለቆቹን የገደሉበት ወይም ማርከው ለንጉሣቸው የላኩበት ቀን አለ ። ዳሩ ግን በግ ራኝ ጥብቅ ተዋጊነትና በመሣሪያው ጥራት ጠቅላላው ድል አብዛኛ ጊዜ በመጨ ረሻ የእስላሞቹ ከመሆን አይዘልም ። እስላሞቹም አሸንፈው በገቡበት አገር አብ ያተ ክርስቲያናቱን ፤ ገዳማቱን ፤ የንጉሡን ከተማዎች የሕዝቡን መንደር እየዘረፉ በማቃጠል ክርስቲያናዊውን ወገን በመፍጀት የልባቸውን ሲሠሩ ኖሩ ።

እንደ እውነቱ የሆን እንደሆን በነዓባ ዓምደ ጽዮን ፡ በነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ ክርስቲያኖቹ ወደ አዳልና ወደ ሱማሌ አገር ባላባቱ ሽፍቶ ለዘመቻ በሔዱ ጊዜ ይኸንኑ የመሰለ ግፍ በተማራኪው እስላም በቤቱ ሰቡም ላይ መሥራታቸው መስ ጊዱንም ፡ መንደሩንም ማቃጠላቸው የታወቀ ነው ። ሲዋጋ በሞተው ተይዞ በተማ ረከው የእስላም መሪ ላይ ግፈኛ አገዳደል እንደሚፈጸሙበት አይካድም ። ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በመሐመድ በድላይ ላይ ያደረጉትንና ከሞተ በኋላ ከሬሳው ላይ የአካሉን መለያልይ እየቆራረጡ ለየአድባራቱ የላኩትን ማስታወስ ይበቃል (1) ። ይሁን እንጂ ባላባቱ በዚህ ዓይነት ከሞተ ወይም ገበርሁ ብሎ ከታመነ ወዲህ ያንኑ ግብር ከመቀበል በቀር ሃይማኖቱን ጨርሶ ለማጥፋት ክርስቲያኖቹ በጊዚያቸው አሁን እስላሞቹ የሚያደርጉትን ያህል ጨክነው ለረዥም ጊዜ ባገሩ ላይ ተቀም ጠው ያሠቃዩዋቸው ጊዜ የለም ። የሆን ሆኖ አሁን የዚህን ጉዳይ ትተን ወደ ዋናው የጦርነት ታሪክ እንመለስና የራስ እስላም ሰገድንና የአዝማች ተክለ ኢየሱስን ፍጻሜ እንመልከት ።

ISIC

ራስ እስላም ሰገድ ከአይፈርስ ጦርነት ተሸንፎ ዛሬ እሚባል ለጦርነት ከማይ መች ፡ አባራሪ ከማይደርስበት ሥፍራ ሆኖ እስላሞቹ ሳይዘጋጅ በድንገት አደጋ ጥለው እንደወጉትና እንዳሸነፉት ለንጉሡ ለዓፄ ልብነ ድንግል ላከ ። ንጉሡም ምንም እንኳን የግራኝን ጦር ጽናት በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ባይዘነጉት በዚህ በአይ ፈርስ ጦርነት ራስ እስላም ሰገድ ብዙ ጦር ይዞ እንደሚገባው ሳይዋጋና ብዙ ጉዳት

(1) ወርአዮ አርዌ በድላይ ዘንተ ኵሎ ደንገጸ ወተሐውከ ልቡ . . . . . ወእምዝ ነደፎ በሐፅ ፩ ብእሲ ገጽ ለአርዌ በድላይ . . . . ወበእንተዝ አውደቆ እግዚአብሔር ታሕተ እዴሁ ወረገዞ በረምሑ . . . . ወእምዝ ነትዑ ኵሎሙ ተንባላት ወደጐንዎሙ ሕዝበ ክርስቲያን እንዘ ይቀትልዎሙ በብልሐ አስይፍት ወነሠኡ ወበጸድፍ እለ ሞቱ ብዙኃን ጥቀ ወኢተርፈ ፩ እምውስቴቶሙ . . . . ወእምዝ መተሩ ርእሶ ለውእቱ ዕልው ዓዲ እዴሁ ወእገሪሁ ወነሥኦ መልክዖ በበመለያልይሁ ወፈነዉ ውስተ ኩሉ አህጉር . . . . . ያዒ ዘርዓ ያዕቆብና ያዒ በዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ፒሩሾ ያሳተመው ገጽ 56 - 65 የኢ.ት. ታሪክ ካዒ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕራፍ ፴፭

በጠላቱ ላይ ሳይጥል እንኳን መሸነፉ ቅር እንዳሰኛቸው በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ላይ ይታያል ።

ራስ እስላም ሰገድ የቀኝ ቢትወደድነት ደረጃ የነበረው መኩንን እንደነበረ ከዚህ በፊት ያነበብነው ትገዛ ይለናል ። አሁን ከርሱ በላይ ሆኖ ለማዝመት የመጣ ውና ከርሱ ጋር የሞተው ተክለ ኢየሱስ የቀኝም የግራም ቢትወደድ ሆኖ የማይ ውቅ አይመስልም ። ነገር ግን ደረጃው ከቢትወደድ በታች ቢሆንም ትግሬ መኩን ንነት ራሱ ከፍ ካሉት ደረጃዎች አንዱ ነው ።

በመጽሐፈ አክሱም መዝገብ ውስጥ በትግሬ መኩንንነት ከግራው አዛዥ ከደ ገልሃንና ከቀኙ አዛዥ ከይስሐቅ ቀጥሎ በሌላ ቦታ ላይ ከደገልሃን በፊት ከቀኝ ብትወደድ ይስሐቅ ቀጥሎ በዚሁ ማዕርግ ስሙ ተጠርቶ ይገኛል (1) ። ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ዓረብ ፋቂህ አዝማች ተክለ ኢየሱስን የእንጎት ገዥ ይለዋል (2) ።

ስለዚህ ዋናውን ጦር አዝማችነት ለትግሬ መኩንን ተክለ ኢየሱስ ሰጥተው ራስ እስላም ሰገድም በደረጃው መዋረድ ቅር ሳይለው ከትግሬ መኩንን ተክለ ኢየ ሱስ ጋር ሆኖ በኅብረት እንዲሠራ ንጉሡ በደብዳቤ አስጠንቅቀው ተክለ ኢየሱስን ከብዙ ጦር ጋር ወደ ዛሬ ላኩ ። ራስ እስላም (እስላም ሰገድ) የቢትወደድነት ማዕርግ እያለው ከርሱ በደረጃ ለሚያንሰው መታዘዙ የርሱ ወታደር ፈርሶ ኅፍረት ስለሆነበ ትና ተክለ ኢየሱስ አዲስ ጦር ስለያዘ ወይም ከዚህ በፊት በባደቄ ጦርነት ከነቢት ወደድ ሠርጼ ጋር ሆኖ ጥሩ የውጊያ ስልት ስለአሳየ ይሆናል ። የሽምብራ ኩሬን ጦር ነትም ከሁለት ዓመት በፊት ተካፍሏል ። እነሆ በሚቀጥለው በርሱ አዝማችነት ክርስቲያናቹ ከግራኝ ጦር ጋር በዛሬ ተዋግተው እንደምን እንደተሸነፉ ተክለ ኢየ ሱስና ራስ እስላም ሰገድም እንደምን እንደሞቱ በዚህ ምዕራፍ ልንመለከት ነው ። ዛሬ የሚባለው ሥፍራ ከዚሁ ከአይፈርስ ምንም ያህል የማይርቅ በዚሁ በደዋር የአውራጃ ግዛት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም ። ስለዚሁ ጦርነት በቀጥታ ዓረብ ፋቂህ የሚለውን ቀጥለን እንመለከት ።

«ይማም አህመድ ከነጦሩ ወደ እንዱራ በደረሰ ጊዜ የሀበሻ ንጉሥ እስላሞቹ የወሰን እስላሞን "እስላም ሰገድን" አሸንፈው እንዳባረሩት ጦሩም እንደፈረሰ የወሰን ሰገድ ቤተ ክርስቲያን እንደተቃጠለች ሰምቶ ትልቅ ኀዘን ተሰማው ። የጦር አለ ቆቹን የቤተ መንግሥት ሹማምንቱን ቤተ ሰቡን ሁሉ ሰብስቦ "እስላሞች በደዋር የሠሩትን ዘረፋ የጦራችንንም መሸሽ ሰማችሁን" አላቸው ። ከዚያም ወደ ትግሬ ልኮ አለቆች ከነጦራቸው እንዲሰበሰቡ አደረገ ። ብዙ ጦር ከብዙ ሹማምንት ጋር

(1) መጽሐፈ አክሱም . . . . . ገጽ 37 ቍ. 46 ገጽ 38 ቍ. 42

(2) እንጎት ከሰሜን ምሥራቅ እንደርታ ከሰሜን አጋሜ ከምሥራቅ ጭድራትና ደንከል ከምዕራብ ሳስታና ከደቡብ ቤተ አምሐራ የሚዋሰነው በጊዜው ትልቅ አውራጃ የነበረ ነው ።

ከተሰበሰቡለት በኋላ ለሁሉም የበላይ ሐሊቃ አዝማች ተክለ ኢየሱስን የአንጎቱን ገዥ ሾመ (1) ።

ይህ ሁሉ ሲሆን እስላም ይማም ከአንጾኪያ ከአባረረው ወዲህ ዛሬ በሚባል ይብዳቢ መግቢያው በሚያስቸግር ሥፍራ ሆኖ ለንጉሡ እንዲዚህ የሚል . . . . . ይብዳቢ ልኮ ነበር ። "ጦሬን በእስላሞቹ ፊት አሰልፌ ላለ ድንገት ብቻዬን ያለጦር በነበር ኩበት ሰዓት አድብተው በተንኮል አደጋ ጣሉብኝ ቢሆንም እስላሞቹ የማረኩብኝ ፈረሶች ጥቂቶች ናቸው" ንጉሡም እንደዚህ ሲል መለሰ "ከአንበጣ የበረከተ ጦር ሰጥቼህ ነበር ነገር ግን አልተጠቀምህበትም አሁን ግን ይኸው አዝማች ተክለ ኢየ ሱስን ልኬልሃለሁና ተከተለው ። የሚያዝህንም ትእዛዝ ሁሉ እየሰማህ ታዘዘው እንጂ እንዳትቃወመው እስላሞቹን ለማጥፋት ረዳት ሁነው ።"

ስለዚህ ተክለ ኢየሱስ ጦሩን አስከትሎ ጉዞ ዠመረ ። በርሱ ውስጥ ፍቅረ ኢየ ሱስ ያኄ እስክንድር (ልጃቸውን ያገባ) አማች የትግሬ የሸሬና የሠራዌ ሹማ ምንት ነበሩ ። በጠቅላላው በውስጡ ብዙ ወታደር ያላቸው ፴ የትግሬ ሹማም ንት ነበሩ ። ከነርሱም ጋር የአንጎት ሕዝብ አብሮ ነበር ። እነርሱም ተጉዘው አዋ ሽን አልፈው በዛሬ ከእስላም ጋር ተገናኙ ። ከዚያ ተክለ ኢየሱስ የበላይነት መሾ ሙን የሚያስረዳውን የንጉሡን ይብዳቢ ለእስላሞና ለጦሩ አነበበ ። እስላሞም እንደ ንጉሡ ቃል እታዘዛለሁ ብሎ ቃሉን አሚን ብሎ ተቀበለ ። ከተክለ ኢየሱስም ጋር አንዱ ኡመር ሁለተኛው ሰካር የሚባሉ እስላሞች ሆነው ሲኖሩ በኋላ ወደ ክር ስትና ዞረው ከንጉሡም ተገናኝተው በሻርካህ አገ[illegible]ታቸው ያንን እያስገበሩ በደስታ ይኖሩ ነበር ። ሚስቶቻቸውም ክርስቲያኖች ነበሩና እስላሞቹ ሻርካህ የነ በሩ ጊዜ ማርከው ወሰደውባቸው ነበር ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ተክለ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ የጦርነት አላቡን ሲረዱ ወደ ይማም አህመድ መጥተው "ባለ ፈው ሁሉ ባጠፋነው በእግዚአብሔር ፊት ተጸጽተናል" ብለው የተክለ ኢየሱስን አሳብ ገለጹለት ። ይማም አህመድ "ግድ የላችሁም አትፍሩ" ብሎ ሚስቶቻቸውን መለሰላቸው ። ቀጥሎም ክርስቲያኖቹ ወደኛ መምጣታችሁን ያውቃሉን አላቸው እነሱም "ምንም አያውቁም" ብለው መለሱለት ። በዚያን ጊዜ ከናንተ ሁለት ነገር እንድታደርጉልኝ እፈልጋለሁ አላቸው ፤ ምን ምን ብለው ጠየቁት "ሰካር ከኔ ጋር እዚሁ ቅር ጓደኛህ ኡመር ግን ወደ ክርስቲያኖቹ ተመልሶ እመካከላቸው ገብቶ ነገሩን ሁሉ ሰልሎ ሄዶን የምንዋጋበትን ሰፈውንና የሚመችውን መንገድ መር ምሮ ተመልሶ ይንገረን ፤ ይኸን ያደረጋችሁ እንደሆነ እግዚአብሔር ያለፈውን ስሕ ተታችሁን ይቅር ይላችኋል" አላቸው ። እነሱም እሺ ብለው ሰካር ከወዚር አዶሌ ዘንድ ቀረ ፤ ኡመር ግን ወደ ክርስቲያኖቹ ዘንድ ተመልሶ በመካከላቸው ሁለት ቀን እድር በሦስተኛው ቀን ወደ ወዚር አዶሌ መጣ ። ወዚሩም ይዞት ወደ ይማም

(1) ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ተድሞ የትግሬ ሹም ሆኖ ቆይቶ በዚህ ጊዜ በዚያው በትግሬ አጠ ገብ የሚገኘውን አንጎትን ተሾሞ ይሁን ወይም በዚያን ጊዜ ትግሬ መኰንን ተብሎ አንጎትን በማዛት መላውን የትግሬን ግዛት በቀራጭነት ጠቅሎ ይገዛ ይሆናል ። የሚመስለውም ይኸው ነው ።

ወሰዶ አገናኘውና ይማም የክርስቲያኖቹን ሐሬ ጠየቀው ። እርሱም “ከክርስቲያኖቹ መካከል ገብቼ እየሁዋቸው መንገዳቸውንም ተረዳሁ ። ከአለፈው አሳባቸው ምንም አልለወጡም” አለ ። ቍጥራቸው ስንት ይሆናል ብሎ ቢጠይቀው ከአንጾኪያው ሽሽት ወዲህ የባሌ ፡ የደዋሮ ፡ የወናግ አምባ ፡ የወናግ ጀደብ (ገደብ) ሰዎች ሁሉም ወደ አገራቸው ተመልሰው አሁን ያሉት አለቆቻቸው ብቻ ናቸው ብሎ መለሰ ። ቢሆንም አሁን ያለው ጦር ምን ያህል እንደሆነ ንገረኝ ቢለው የትግሬ የአንጎት የፈጠጋር ሰዎች አሉ አለ ። ስንት ፈረስ አላቸው ብሎ ቢጠይቀው ፳፻ የሚሆኑ የሪፍ (1) ፈረሰኞች ሁሉም ብረት ለበስ (ጥሩር) የሆነውን እንደለበሱ አሉ ብሎ መለሰ ። ያሉበት ሥፍራ ሰፊ ነው ጠባብ ለፈረሰኛ ጦርነት ይመቻል አይመችም ብሎ ቢጠይቀው ከዚህ አሁን ካለንበት ተነሥተን ወደ እነሱ ብንሔድ እሰፊ ሥፍራ ላይ እናገኛቸዋለን ካንድ ቁልልታ ካለበት ወገን የመግንባቸው እንደሆን ግን እየገፋናቸው ወደ ወንዝ እንወርዳለን ፡ ክርስቲያኖቹም የያዙት የላይኛውን ሻረት ነው ፡ እነሱ የሰፈሩት እቁልልታው ጫፍ ስለሆነ ከግርጌው ትልቅ ገደል አለ ብንወጋቸውና በአላህ ፈቃድ ድሉን ብናገኝ ከቁልልታዋ ላይ ሲሸሽ የፈለገ ሁሉ ገደል ገብቶ ይሰባበራል እንጂ መሸሻ ቦታ የለውም ብሎ አስረዳው ።

ከዚህ በኋላ ይማም ፈረሰኞቹን አስጠራና ከሰላዩ የሰማውን ገለጸላቸው ። ከእነሱም መካከል ግማሹ እዚህ እንዳለን ክርስቲያኖቹን ጠብቀን እንውጋ የቀረው አሉበት ድረስ ሔደን እንውጋቸው ሲባባሉ ይማም የናንተ አሳብ በፍጹም አያረባም ብሎ እዚሁ ቀርተን ክርስቲያኖቹ ሲመጡብን እንዋጋ ያሉትን ነቀፈና ይልቅስ የማግረብ ጸሎት (2) ካደረግን በኋላ እንንዝ አለ ። እነሱም ፈቃዳችን ነው ብለው መለሱለት ። ስለዚህ ይማም እንደ ጎርፍ የሚፈስውን ሠራዊቱን እፊት አስቀድሞ እርሱ ከኋላ ሆኖ ከማታ ገምሮ ጎሕ እስኪቀድ ድረስ ተጉዘው ክርስቲያኖቹ ወዳሉበት ቀበሌ ደርሰው ዕረፍት ሆነ ። በዚህ ጊዜ ይማም መንገድ መሪውን ልኮ እፊቱ አስመጣና አብረን እንሂድና መንገዱን እየመረመርን ሥፍራውን እንስልል ቢለው እኔ በጣም ያክሜአለሁ ነገር ግን አንድ አርኪያህ የሚባል ወደ እስልምና የዞረ የክርስቲያን ሹም መንገዱን የሚያውቅ አለ ብሎ መለሰ ። ይማም አርኪያህን አስመጣና እርሱን እንደያዘ ሌሊቱን ሄደ ። ከርሱም ጋር ገራድ ሻሙንና ማታን ነበሩ ። እንደ ሔዱም የውሻ ጩኸት የመሰለ ሰሙና የምን ጩኸት ነው እየተባባሉ ሲጠያየቁ እናንተ እዚሁ ቆዩ እኔ መርምሬ እመጣለሁ ብሎ አርኪያህ ጩኸት ወደተሰማበት በኩል ሲሔድ ውሻ የሚጮኽበት መንደር አየ ። አርኪያህም “እናንተ የመንደር ሰዎች !” ብሎ በታላቅ ድምፅ ተጣራ እነርሱም “እረ ማነህ በጭለማ የምትጣራ !” ቢሉት እኔ ከደዋሮ የመጣሁ ሹም ነኝ ብሎ መለሰላቸው ። እኋላህ ያሉት እነማን ናቸው ቢሉት ወታደሮች ናቸው ተክለ ኢየሱስ እስላሞችን ለመውጋት እንድ

(1) ከሰሜን አፍሪካ የመጡ ይሆኑ ሪፍ ምን ማለቱ እንደሆን አይገባኝም ፤
(2) ማግረብ በዓረብኛ ምሽት በኛ በግዕዙ ዓርበ ጠለቀ ብሎ ዕርበት ምሽት እንደሚለው ስለሆን እዚህ ላይ የማታ ጸሎት ማለቱ ነው ።

ትረኛ ወታደርህን ይዘህ እንድትመጣ ብሎ ልኮብኝ ነበር ሲል መለሰ ። በዚያን
ጊዜ መንደረተኞቹ ወደ ኋላህ ተመለስና እስከ ጉብታው ድረስ ሂድና እዚያ ስትደ
ኋ ወደ ሸለቆው ሥር ወርደህ ወደ ቁልልታው ስትወጣ ተክለ ኢየሱስን እዚያው
ሥፍሮ ታገኘዋለህ አሉት ።

ይኸን ሁሉ ከሰማ በኋላ ወደ ይማም ተመልሶ ነገረው ። ክርስቲያኖቹ እዚያው
የመዠመሪያው መንገድ መሪ እተናገረበት ሥፍራ ላይ መሆናቸውን ጨምሮ ገለጸ
ለት ። ስለዚህ እስላሞቹ በደስታ ወደ ሠፈራቸው ተመልሰው ለጓደኞቻቸው ነገሩና
ጨርሶ እስኪነጋ እዚሁ ቆይተው ሲነጋ የጧት ጸሎታቸውን አድርሰው ሲጨርሱ
ወዚር አዶሌ ግንባር ቀደም ሆኖ ከነጠሩ መንገድ መሪው እፊት እፊት እየመራ ጉዞ
ውን ዠመረ ። እነርሱም ከጉብታው ወርደው እሸለቆው ሲደርሱ የክርስቲያኖቹን
ድንኳን አዩ ። ክርስቲያኖቹም እስላሞቹ ወደ ሸለቆው ሲሽቆለቆሉ ዓይተዋቸው
ኖር ከርቻቸውን ጭነው ወደ እስላሞቹ መጡ ።

ይማም ሌላው ወታደር እስኪለጥቅ ድረስ እሸለቆው ሆኖ ይጠብቅ ነበር ። እነ
ሰበርዲን እነ ዓሊ እነ አብደላ እነ አዴቅ ሌሎችም ፭ የሚሆኑ ይማምን ሳይጠብቁ
ወንዙን ተሻግረው ነበር ። ከነርሱም ጋር እነ ፈንጅ ሰበር ያሉበት ፴ የሚሆን የእግ
ረኛ ጦር ነበርና እነዚህ ከክርስቲያኖቹ ጋር ጦርነቱን ዠመሩ ። ወዚር አዶሌ ግን
ይማም እስኪደርስለት እሸለቆው ሆኖ ሲጠብቅ በደረሰለት ጊዜ ሁሉም እፈረሶቻ
ቸው ተጋቡና ሽቅቡቱን ወጥተው እጫፍ ካሉት ከክርስቲያኖቹ ጋር ተጋጠሙ ጦር
ነቱን የዠመረው ሰበርዲን ነው ። ከርሱም ቀጥለው ዓሊ[illegible] ዋራዲና አብደላ ተከ
ታትለው እጠላት ጦር መካከል ገቡ ። አደቅ ቤን ማሂና አሊ ጎይታም ሁለቱ ባንድ
ነት ገሥግሠው ተክለ ኢየሱስን ውጊያ ገጠሙትና አዴቅ ሰይፉን መዞ ተክለ ኢየ
ሱስን በሰይፍ በትር እንገቱን መትቶ ጭንቅላቱን ከሌላው አካሉ ለይቶ ጣለና ገደ
ለው ። ይማምና ጓደኞቹም ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ጋር ተጋጥመው በጥብቅ ሲዋጉ
ክርስቲያኖቹ ሽሽት ዠመሩ ። እስላሞቹም እየተከታተሉ መግደልና መማረክ
ዠመሩ ። እስላም (ራስ እስላም ሰገድ) በገራድ ይማጅ ልጅ በአቡበከር እጅ ተገ
ደለ ። ናስር የሚባለው የመርጋ (ጃ) ሹምና ሹተላይ የሚባለው ሹም በፋራቃሃም
ዓሊ እጅ ተማረኩና ሹተላይና ናስር ወዲያው እስላም ሆነው ወደፊት እንደሚገ
ኘው ከክርስቲያኖች ጋር እየተዋጉ ሹተላይ ሞተ ።

በዚሁ ጦርነት ነገደ ኢየሱስ የሚባለው የጂናህ (ጊና አገር ?) አገረ ገዥ በገ
ራድ አህሙሹ እጅ ፤ ዘምቢል የሚባለው የቡሬ ሹም በአቡበከር እጅ ፤ የሲሬ (ሺሬ)
ሹም ሳሙኤል ባንድ እስላም እጅ ፤ አብርሃም የሚባለው የጸለሞት ሹም በአብሳማ
ኡር እጅ የሐማሴን ሹም በሳሊህ እጅ ተገደሉ ። እሰር (አሥራት ?) የሚባለውን
ሹም ባህር ፤ ከፍሌ የሚባለውን የቅዳ ሹም (የተክለ ኢየሱስ ልጅ) ሀሰን ፤ ጊዮር
ጊስ የሚባለውን የጉጃም ገዥ የፈራቃሃም አሊ ወታደር ማረኩዋቸው ። ይስሐቅ
የሚባለው የበጌምድር አገረ ገዥ አሊ ማጅራህ በሚባል ሱማሌ እጅ ሞተ ። በዚህ
ቀን ጦርነት የሞቱት የትግሬና የአማራ መኳንንት ቊጥራቸው ፩፻፴ ነው ። የም
ተው የፈረሰኛና የእግረኛ ወታደር ግን በብዙ ሺ የሚቆጠር ነው ። ፭ ፈረሰኛ ብቻ

ሲያመልጥ ፷፪ ፈረሶች ድንኳኑ ባሪያው በቅሎውም ዕቃውም ሁሉ በእስላሞች እጅ ወደቀ ።

ወዚር አዶሌ ከዋናው ጦር ጋር እዚሁ እክርስቲያኖቹ ሠፈር እቀልልታው ላይ ሠፈሩን አድርጎ ሲቀመጥ ይማም ፶ ፈረሰኛ ይዞ የሸሹትን እስከ አዋሽ ድረስ አባሮ ድል ሜዳ ላይ አደረ ። በማግስቱ አብድ ኢን ናስርን ከንዝ ጋር ወደ ተወበት ወደ አንዱራህ ሔደና ከዚያ ከናስር ጋር ጃሚት ወደ ሚባለው ሥፍራ ሔደ ። ወዚር አዶሌም ከነበረበት ሠፈሩ ተነሥቶ በሁለተኛው ቀን ወደዚሁ ጃሚት (ሀሚት) መጣና ሁሉም ሰላምታ እየተሰጣጡ ተገናኙ ስለአገኙትም ድል በደስታ እየተነጋገሩ ሌሊቱን በዚሁ ሥፍራ አሳለፉ ።

በማግስቱ ይማም የተማረከውን ሰውና ፈረስ መሣሪያ አቅርቡልኝ ብሎ አዘዘ ። ፷፪ ፈረሶች በቀይ በተጠለፈ እንደ ብርሃን ጮራ በሚያበራ በወርቅ ዕቃ የተጫኑ ኮርቻቸው ሐር የለበሱትን አቀረቡለት ። ዳዊት ይለብሰው እንደ ነበረ ያለ (1) ብዙ የጥሩር ልብስ በራስ ላይ የሚደፋ እንደ ሳቡር (አገር) ያለ የግብጽ አገር ሥራ የሆነ ብዙ ሰይፍ ነጭ ቅርጫት የሚመሳስል የሀበሾቹ ጋሻ ቀረበ ። ይማም ልዑል እምላኩን አመሰገነ ። ከምርኮው ሁሉ ከበቅሎም አምስተኛውን ዕጣ እያስነሣ በቅሎውን ፈረሱን ስለሃይማኖታቸው ለሚዋጉት አደለው ። በሽምብራ ኩሬ ጦርነት የዋለው አንድ ተናጋሪ "ከይማም ጋር በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ላይ ውያለሁ ነገር ግን እንደዚህ እንደዛሬ የሚያምሩና የሚበረክቱ በቅሎና ፈረሶች በፍጹም አላየሁም" ብሏል ።

ISIC

ከእሥረኞቹም የሹተላይና የአሰር (እሥራት) ጭንቅላት ተቆረጠ (2)፣ ክፍሌ በ፴ ወቄት ወርቅ ወገኖቹ ገዙት ፣ ጊዮርጊስ የሚባለው ግን ሁለት ወር ታስሮ እንደ ቆየ እግር ብረቱን ሰብሮ ጠፋና ወደ ጐጃም ሔዶ ሳለ አንድ ክርስቲያን ገደለው ። ለጊዮርጊስ ወንድም ይማም ምሕረት አድርጎለት ከዚያም ደብዳቤ እሲዞ "ይኸን ደብዳቤ ይዘህ ሔደህ መልሱን አምጣልኝ" ብሎ ወደ ወናግ ሰገድ ወደ ሀበሻ ንጉሥ ላከው ደብዳቤውም እንደዚህ የሚል ነው ።

"በእግዚአብሔር በመሐሪውና በይቅር ባይው ስም ምስጋና ለእግዚአብሔር ብቻ ደኅንነትና ቡራኬ ለነቢዩ ለመሐመድ ከርሱ በኋላ ሌላ ለማይነሣው የተላከ ከይማም አህመድ የኢብራሂም ልጅ ስለ ሃይማኖቱ የሚዋጋ ይድረስ ለሀበሻ ንጉሥ ከሰላምታ በኋላ ለላይኛው ንጉሥ (እግዚአብሔር) ቀጥ ያለውን መንገድ ይዞ የሚታዘዘውን (3) ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ ፋኑኤል የማረካቸውን አቡበከር ቢን ሞስሊምንና ጃልቲን ላክልኝ እኔም በነርሱ ምትክ ጊዮርጊስን ፤ ክፍሌን ፣ ናስርን ፣ የኤል ሜርጃይ ጌታ ሹተላይን አራቱን እልክልሃለሁ ። እስላም እስላምን ክርስቲ

(1) ዳዊት የጀኤል ንጉሥ ወይም ልብነ ድንግል እንዱ ስመ መንግሥታቸው ዳዊት ስለሆነ እርሳቸው የሚለብሱት ማለቱ እንደሆነ አይታወቅም ።
(2) ዓረብ ፋቂህ በፊት ሹተላይን ተለቀቀ ካለ በኋላ አሁን ደግሞ ተገደለ ይለዋል ።
(3) ፩ኛ ሳሙኤል ምዕ. 17 ቍጥር 38

ያን ክርስቲያንን ስለሚረዳው እኔ ሁለት ስጠይቅህ ላንተ የምሰጥህ አራት ናቸው
እንደ ቀድሞ አንድ ጊዜ ባገር ገብተን ተመልሰን ወደ አገራችን የምንመለስ አይም
ሰልህ አገሪቱን በእግዚአብሔር ፈቃድ በሙሉ ድል አድርገን እስክንይዝ ድረስ
እንመለስም ። እዚሁ ለመሞት ቆርጠናል ስለዚህ እውነተኛው ዳኛ በመካከላችን
ይፈርዳል ።"

ይቺን ደብዳቤ አጣጠፈና ወስደህ ለንጉሡ ስጥ ብሎ እሥረኛውን የጊዮርጊ
ስን ወንድም ላከውና ሄደ ። እርሱም ወደ ንጉሡ ደርሶ ደብዳቤውን አስረከበ ። ንጉ
ሡም ደብዳቤው የሚለውን በተመለከተ ጊዜ በኩራት እየተሳደበ ፊቱ ፍም እስኪ
መስል ድረስ በታላቅ ኃይል ተቆጥቶ ዘውዱን ከራሱ ላይ አንሥቶ እመሬት ወረወ
ረው ። በንዴትም ምርኮኞቹን እስላሞች አራቱ አስመጥቶ አስገደላቸው ለደብዳቤ
ውም ምንም መልስ አልሰጠም» (1) ።

ባለፉት ምዕራፎች ግራኝ አህመድ በመሣሪያ ልዩነት በሥፍራ አመራረጥ
ድሉን ማረጋገጡን እንደተመለከትነው በአሁኑ ምዕራፍ ደግሞ ይህ ሁሉ ሳይቀር
በዚህ ጊዜ ከቀድሞው የበለጠ በሰላይ በኩል ደህና አድርጎ መጠቀሙን እናያለን ።
እነዚያ ኡመርና ሰካር የሚባሉ ሁለት ቀድሞ ከእስላምነት ወደ ክርስቲያንነት
አሁን ደግሞ ከክርስቲያንነት ወደ እስላምነት የተመለሱት የክርስቲያኖቹ ወገን
መስለው ብዙ ዘመን አብረው ከኖሩ በኋላ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ እስላሞቹ ሲቀናቸው
ክርስቲያኖቹ መሸነፍ ሲበዛባቸው ዓይተው በሥውሮSወ ዩ ግራኝ ገብተው ብዙ
ምሥጢርና ወሬ ሲነግሩት ለግራኝ የጦርነት ፕላን በጣም ጠቃሚ ነው ። ለግራ
ኝም ሁለቱ ወደ እርሱ መግባታቸው እስከዚህም ጊዜ ድረስ ያወቁትና የነገሩት ሳይ
በቃው ቀርቶ ከሁለት አንዳቸውን ሰካርን እንደመያዣ አስቀርቶ ኡመርን መልሶ
ወደ ተክለ ኢየሱስ ሠፈር ልኮ ሲያሰልል ግራኝ እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ ያለ
ውን የጠላቱን የተክለ ኢየሱስን አሳብና በትክክል የሚገኝበትን ሥፍራ የጦሩን
ቍጥር ለማወቅ እንደፈለገ ዑመርም በክርስቲያኖቹ መካከል እንደ ወገን አብሮ
እየተጫወተ ሁለት ቀን ሙሉ የጦር ፕላን ሲሰበስብ መንገድና ለጦርነት ምቹ
ሥፍራ የሆነውን ሲያጠና ሰንብቶ ወደ ሃይማኖት ወገኖቹ ተመልሶ ያየውን የሰማ
ውን ለግራኝ ነገረው ። እንደዚህ ያለውም ስለላ በጦርነት ሰዓት አገልጋይ በመሆኑ
ከቀድሞ ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ያሉ መንግሥታት የየጠላታቸውን ምሥ
ጢርና አሳብ ለመረዳትና የጠላት ጦር የሠፈረበትን ለማወቅና ለነገሩ መድኃኒትና
መውጫ ለመፈለግ ብዙ ደም ብዙ ገንዘብ እያፈሰሱ ይታገሉበታል ።

ግራኝ አብ ወደ ክርስቲያኖቹ ተጠግተው በሚኖሩት እስላሞች ብቻ ሳይሆን
ዛኛው ጊዜ በተማረኩ ክርስቲያኖች መጠቀሙን ባለፉት ምዕራፎች ተገንዝበ
ናል ። አሁንም በዚህ ምዕራፍ አዝማች እርኪያህ ወገኖቹን ከድቶ የተማረከች ሚስ
ቱን ለማግኘትና ከአሸናፊው ጋር ለመለጠፍ ሲል በእንዴት ያለ ትክክለኛ መን
ገድ እስላሞቹን መርቶ ወደ ክርስቲያኖቹ የጦር ሠፈር እንደ ወሰዳቸው የክርስቲያ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 195 - 206

ኖቹን የዋሃን መንደረተኞች "እኔ የደዋሮ ሹም ነኝ ተክለ ኢየሱስን ልረዳ መጥቼ መንገድ ጠፋብኝ" እያለ እየሙኘ ተክለ ኢየሱስ የሠፈረበትን ቦታ በትክክል ለማወቅ እንዴት አድርጎ እንደአታለላቸው ተመልክተናል ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ ከክርስቲያኖቹ ጋር በነበሩት እስላሞች የሃይማኖት ወንድምነትን እያሳየ ለተማረኩት ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ በማስፈራራት ሲያስፈልግ ሹመትን በመስጠት የተማረኩ ሚስቶችንና ልጆችን በመመለስ መልካም ኑሮን እያመለከተ በጊዜና በአጋጣሚ ነገር መጠቀም የሚያውቅ ትጉህና የወጣለት ጠንቃቃ መሪ መሆኑን በየጊዜው እንገነዘባለን ።

እንደዚህ ያለውም ጠባይ ከጥብቅ ተዋጊነትና ከዠግንነት ጋር ተደባልቆ ያንድ ሰው ሀብቱና ስጦታው ሲሆን በመሣሪያ በዠግንነት በትጋት የሚበልጠው እስኪገኝ ወይም ራሱ የአፍላው ጊዜ እልፎ አእምሮው እስኪደንዝ ድረስ ለዚህ ሰው ሁል ጊዜ የአሸናፊነት በር እንደ ተከፈተለት ነው ። ፲፭ ዓመታት ኢትዮጵያን በያለበት እያመሰ ከገዛ በኋላ በመጨረሻ አዳዲስ መሣሪያ የያዙ ፖርቱጋሎች በመጡ ጊዜ ይህ ሁሉ ትጋትና ጥንቃቄ በርዶ ያገር ጌታ በመሆንና በመቀማጠል ሲዘነጋና ሲሸነፍ ወደፊት ይታያል ። ክርስተያኑ ንጉሥ ባለፈው ጊዜ በንኤሚር ማኅፉዝ ላይ አግኝተውት የነበረው ድል በግራኝ ጊዜ እንዳዘነጋቸው እርሱ ደግሞ በተራው በርሳቸው ላይ ያገኘው የተደጋገመ አሸናፊነት አኩርቶት በፖርቱጋሎቹ አመጣጥና አወጋግ ጊዜ ዡን ጋታና ንቀት አድሮበት ዞሮ ዞሮ እርሱም በርሳቸው የዘንጋታና የመዝናናት ስሕተት መውደቁን በሥፍራው ስንደርስ እንመለከታለን ።

ከዚህ አልፈን ግራኝ ላቄ ልብነ ድንግል የጻፈውን ደብዳቤ ስንመለከት አገሪቱን በሙሉ ድል አድርጎ ለመውረር ቁርጥ አሳብ አድርጎ መነሣቱን እንረዳለን ። በአራት ክርስቲያኖች ሁለት እስላሞች ለመለወጥ ማሰቡ የእስላሞቹን ሕይወት ከክርስቲያኖች ማስበለጡን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ዛሬ የምለቃቸው ክርስቲያኖች ነገ ተመልሰው በእጄ መውደቃቸው አይቀርምና እስከዚያ በተማረኩት በሁለት እስላም ሹማምንት አደጋ እንዳይደርስባቸው ላድናቸው ብሎ ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል ምንም በብዙ የጦር ግንባር እንደቀናው ቢያውቁ ለግራኝ አሳብና ምኞት አሳባቸውን አላሉም ። እንዲያውም ይህ የንጉሥነት ዘር የሌለው ጊዜና የጦር ግንባር ያነሣው ሰው ይኸን የመሰለ የዛቻ ደብዳቤ ደፍሮ በመጻፉ በጣም ተናደው ሌላ ምንም ማድረግ ስለአልቻሉ ከንዴታቸው ብዛት የተነሣ ዘውዳቸውን ከራሳቸው አንስተው ወርውረው ለዚህ ደብዳቤ ለዚህ መደፈር ምክንያት የሆኑትን እስላሞች አስገድለዋል ማለት ነው ። ለደብዳቤውም መልስ አለመስጠታቸው ከርሱ ጋር በመጻጻፍ ንጉሣዊ ክብራቸውን ለርሱ ዝቅ አድርገው ላለማዋረድና በጠቅላላው "አላውቅህም" በማለት ያሰቡ ይመስላል ።

ይኸም ሁኔታ ባንድ ተከብሮ ተፈርቶ በኖረ ንጉሥና ጊዜ ባነሣው ተራ ሰው ዘንድ ሲፈጸም የኖረ ነውና አያስደንቅም ። ዓፄ ልብነ ድንግል ከሰሎሞናዊው ዘር ከይሁና አምላክ የወረዱ አባቶቻቸው እነ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ፣ እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሰፊውን የኢትዮጵያ መንግሥት በንጉሠ ነገሥትነት ሲገዙ የይፋትን የአዳልን የእ

ሰላም ባላባት እንደሌላው አውራጃ እንደ ደዋሮ እንደ ሐድያ ሲያስገብሩ የኖሩ ናቸው ። ራሳቸው ባባቶቻቸው አሊጋ ከተቀመጡ ወዲህ ማኅፉዝ የሚባለውን የግራኝን ሚስት የድል ወንበራን አባት ከአሸነፉ ወዲህ ያባቶቻቸው ሥል ጣንና ክብር በርሳቸው እጅ በሆነበት ዘመን በጦር ግንባር መሸነፍን እግዚአብሔር ሳይታሰብ እንደመዓት የጣለባቸው ብቻ መሆኑን ቢያምኑም ካንድ ዘሩ ካልታ ወቀ ይማም አህመድ ከሚባል ጋር ደብዳቤ መጻጻፉ ሊዋጥ የማይቻል መራራ ጉርሻ ሆኖባቸዋል ማለት ነው ።

ያንድ ሰው አነሣሡ የጦርነት የመሸነፍና የማሸነፍ አመጣጡ ብዙ ጊዜ አይታ ወቅም ። እንደዚሁ እንደ ዓፄ ልብነ ድንግል የጀርመንና የኤስፓኝ ንጉሠ ነገሥት ሻርል ፭ኛ ከቱርኩ ሱልጣን ጦር ጋር በ፲፭፻፵፩ ዓ.ም. እ.አው. ቀ. አልጀሪ ላይ የመ ርከብ ጦርነት ዝምሮ የባሕር ውሽንፍር ባንድ ወገን የቱርክና የዓረቦች ውጊያ በሌላ ወገን ሆነው በሁለት ወገን አስቸግረውት ስለተሸነፈ አልዠሪን ለመያዝ ያለ መው ዓላማ ሳይሆንለት ተናዶ ወደሰፊው ግዛት ወደ አውሮፓ በመጣበት መርከብ ሲመለስ "ሂድ ከኔ ምስኪን መጫወቻ ሌላ የታደለ መስፍን አግኝቶ ይሸከምሁ" ብሎ በስንት ጌጥ የተሠራውን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዱን ወደ ባሕር ወረወረው ይባላል (1) ።

ነገር ግን የሻርል አምስተኛ ንዴትና ያፄ ልብነ ድንግል ብስጭት መንገዱ የተ ለያየ ነው ። ሻርል አምስተኛ በሰፊው የቄሣር ግዛት ( "Saint Empire Romain") ISIC በሚባለው በጀርመን ፤ በኤስፓኝ ፤ በነምሳና በኢጣሊያ አጋማሽ ሰፋፊ ግዛቱ ላይ የአፍሪካን ሰሜን ከቱርክ ላይ ለመቀማትና ግዛት ለማስፋፋት ነው ። የዓፄ ልብነ ድንግል ጸጸት ግን የውጭ አገር ስም ያለው ንጉሥ እንኳን ከውጭ መጥቶ ሳይወጋ ቸው አንድ አልባሌ የነበረ ሰው ግዛታቸው ከነበረው ከአዳልና ከሐረር ተነሥቶ ከቤተ መንግሥታቸው አባርሮ ከአውራጃ ወደ አውራጃ የሚያሳድዳቸው ስለሆነ የሁለቱ ሁኔታ በዘውድ አጣጣል ይመሳሰል እንጂ የንዴቱ ሰበብ በፍጹም የተለያየ ነው ።

## ምዕራፍ ፴፰

### ከአይፈርስና ከዛሬ ጦርነት በኋላ የግራኝ ጉዞ ወደ ዝቋላ — በዝቋላና በባይቄ በአን ዶጥና የቤተ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መዘረፍና መቃጠል ።
### (ሚያዝያ - ሐምሌ ፲፭፻፴፫ ዓ. ም.)

ከአይፈርስና ከዛሬ ጦርነት በኋላ ከደብዳቤው ላይ እንደተረዳነው ግራኝ አህመድ ወደፊት እየገሠገሠ ንጉሠ ነገሥቱን ለመውጋት አገራቱን ለመውረር እንጂ እንደ አለፉት ዓመታት አንድ ከፍ ያለ የጦርነት ድል ባንድ የጦር አለቃና አውራጃ ላይ

(1) Soliman le Magnifique-Fairfax DOWNEY ገጽ 167

ባገኘ ቍጥር ወደ አገሩ ወደ ሐረር ለመመለስ አልፈለገም ። የማይመለስበትም ምክንያት አንደኛ ባሁኑ ሰዓት ለድል የሚያስተማምኑ መድፎችና ጠመንጃዎች የያዙ የዓረብና የቱርክ ሌሎችም ዘራቸው ልዩ ልዩ የሆነ የእስላም ወታደሮች ከማዶ ከሰፊው የቱርክ ግዛት ከጅዳ ፣ ከየመን ፣ ከዘቢድ ፣ ከአደን እየተነሡ የርሱን ድል አድራጊነት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በተለይም ከየቤተ መንግሥቱ የሚገኘው የሀብት ምርኮ ብዛት ስቧቸው እየመጡ ባጠገቡ በርክተውለታል ። ሁለተኛ በነዚህ ዙሪያ ደግሞ መሬሃን ጊሪ ሐርላሀ ሀብር ማጋዲ መለሳይ እየተባሉ በየነገዳቸው የሚጠሩት የሱማሌና የአዳል ተዋጊ ሕዝብ ከወዲህም ቀድሞ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እየገበሩ ይኖሩ የነበሩት የሐድያ የደዋሮ የይፋት የባሌ እስላሞች ከነዚያ ጋር በመተባበር የቀረውም ክርስቲያናዊ ሕዝብ ይኸን የመሰለ የተደጋገመ መሸነፍ በንጉሡና በመኳንንቶቻቸው ላይ በመድረሱ ከተዋጋም በኋላ ሳይዋጋም ሁኔታው እያስገደደው በመስለምና ወደርሱ በመግባት በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥቱ ጕራ በላላ መጠን የርሱ በጣም በመጠንከሩና ምንም የሚሰጋበት ኃይል ባለመኖሩ ነው ።

ጊዜ ለሰጠው ባለሥልጣን መሣሪያ መሆን ከልባቸው ደስ የሚላቸው አድርባዮች እንደነ እርኪያሀ ወደፊት እንደምናያቸው እንደነ አናንያ እንደነ አዝማች ሃይቢ ያሉት ከእንግዲህ ወዲህ አስፈሪ ኃይል አለመኖሩን ከማስረዳት ጋር ባሸናፊው በግራኝ አህመድና በሹማምንቱ ፊት ሞገስ ለማግኘት የራሳቸውን የቤተ ሰባቸውን አቅዋም ለማጽናት እኔ መንገድ እመራለሁ ፤ እኔ አገሩን አውቀዋለሁ እያሉ የሚያስተናብሩ ሞልተዋል ። ከነርሱም ጋር ቀድሞውኑ እስላሞች የንጉሠ ነገሥቱ አገልጋዮች ወይም ገባሮች የነበሩት አሁን የሃይማኖት ወገኖቻቸው አሸንፈው አገሪቱን ሲይዙ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ ተደስተው ለግራኝ ወረራ ዋና መሣሪያ መሆናቸውን አልፎ አልፎ በዚሁ በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ባለፈው የተጠቀሰውን እናስታውሳለን ።

በዚህ ምክንያት በአይፈርስና በዛሬ ከፍ ያለ ጦርነት ተደርጎ አሁንም ግራኝ አሸናፊ ሆኖ እነ ራስ እስላም ሰገድ ፣ እነ ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ከሞቱ ወዲህ የሆነውን ዓረብ ፋቂህ በሚሰጠው ዝርዝር ውስጥ ፦

ሀ . ግራኝ አህመድ ከነጦሩ ገሚት ከሚባል ሥፍራ ወደ ቃንቡራ በሄደ ጊዜ በገበያ የነበረው ሰው ሁሉ በክብር ተቀብሎ እንዳስተናገደው ፤

ለ. የሱማሌ ወታደር እንግዲህ በብዙ ምርኮ ገንዘብና ሀብት ስለከበርን ከኢማም አህመድ ተደብቀን ወደ አገራችን እንመለሳለን ማለታቸውን ሰምቶ ግራኝ በመካከላቸው ሰላይ እንዳስቀመጠ ፤

ሐ. አዝማች ሐይቢ (ሐይብ) የሚባለው የጋቱር ገዥ ንጉሡ ሽረውት የነበረው አሁን ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ መሞቱን ሳይሰሙ ንጉሡ ተክለ ኢየሱስን እርዳ ብለው ልከውት ሳለ ዘወር ብሎ ወገኖቹን ከድቶ ለግራኝ ገብቶ መስለሙን ይኸው ሰውዬ ለግራኝ አህመድ ከማናቸውም ከዳተኛ የበለጠ በጦርነትም ወሬ በመስጠትም መንገድ በመምራትም እንደረዳው ፦

መ. ዓምዱ የሚባለው በግራኝ እጅ የነበረው ምርኮኛ በግራኝ አህመድና በደዋሮ ሹማምንት በአዳሉ በፋኑኤል በጊዮርጊስ በድል ሰበር መካከል ገብቶ ግራኝ ግብሩን ሊቀበል እንጂ የደዋሮን አገር ላያጠፋ ፤ እነሱም ሊገብሩ እንጂ ላይዋጉ ይኸንንም ዕርቅ የተደራደሩት ከዳሞት ሊዋጋ የመጣው ታላቁ መሪ ራስ ወሰን ሰገድ ሳይሰማ መሆኑንና ከዓምዱ በኋላ ይኸንኑ እርቅ ወደፍጻሜ ያደረሰው ዚን የሚባለው መሆኑን ፤

ሠ. የዛሬ ጦርነት ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ገበርጌ ወጅ (የዛሬው ወንጂ) ሳሉ የጦራቸውን መሸነፍ ሰምተው እንዳዘኑ ። አሁንም እስላሞቹ ይኸን ያህል ምርኮ ስላገኙ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ መስሏቸው እንደነበረ እስላሞቹ ግን ወደሐረር በመመለስ ፋንታ ከአይፈርስ ወደ ኤልማያ (ዝቋላ ዙሪያ) እንደተጓዙ ። በጉዞም ላይ ግራኝ "የኤልማያ ሕዝብ ከነብት በቀር ምንም የለውምና በመርዛም ቀስቱ እየወጋ እንዳያስቸግረን ከብቱን አትንኩ" የሚል ትእዛዝ ለወታደሩ መስጠቱን ፤ ቀጥሎ የተከተለው ጦር ሠራዊት እያንዳንዱ ብዙ (፪፻) በቅሎና ባሪያ የምርኮ ዕቃ የያዘውን ዓይቶ ይኸን ሁሉ ይዛችሁ እንዴት አድርጋችሁ ከክርስቲያኖቹ ጋር ትዋጋላችሁ ብሎ ባሪያና በቅሎ ያለው ይጫን እንጂ አንድም (ተዋጊ) ሰው በእጁ ዕቃ እንዳይሸከም አዝዣለሁ ትእዛዜን የተላለፈውን ጭንቅላቱን እቆርጣለሁ ብሎ በቁጣ ማዘዙንና ወታደሩም እየተላቀሰ የያዘውን ሁሉ ስለጣለ ሸለቆውና መንገዱ ሁሉ በ[illegible] በባሪያ መሙላቱን (1)

ረ. እስላሞቹ ከአይፈርስ (ደዋሮ) አልፈው በፈጠጋር ግዛት ወደሚገኘው ወደ ተራራ ሥር ማርዚር መድረሳቸውን ይኸም አገር ዛቃላህ (ዝቋላ) ከሚባለው ተራራ ሥር የሚገኝ መሆኑን በርሱም ላይ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረ የእስላሞቹን መጠጋት ሲያዩ ጠባቂዎቹ በውስጡ ያለውን ዕቃና ልብስ ሰብስበው ወደ ተራራው ሲሸሹ እስላሞቹ እየተከታተሉ ሰዎቹን ገድለው ዕቃውን እንደዘረፉ ሌሎቹም በቤተ ክርስቲያኑ እሳት ለቀውበት ስለነበረ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ሁለት ቀን የሚያስኬድ እርቀት ባለው አገር ሆነው ቃጠሎውን በሩቅ ስለተመለከቱ እስላሞቹ ወደኛ ይጓዛሉና ድረስ ብለው ዳሞት ለሚገኘው ለአውራይ ኡስማን ለስመ ጥሩው የጦር አለቃና መኰንን ለራስ ወሰን ሰገድና ለአውራይ ኡስማን ስለታየ በባ እንደላኩ ቀጥለው እስላሞቹ ከዝቋላ ወደ ዱከም መምጣታቸው ስለታየ በባደቱ ከተማ ያለውን ከቤተ ክርስቲያኑ በቀር ቤተ መንግሥታቸውን እስላሞቹ እኛ አቃጠልነው ከሚሉ አቃጥሉት ብለው ማዘዛቸውን ፤ የንጉሡ ሹም ቤተ መንግሥቱን አቃጥሎ ሲመለስ ወዲያው ደግሞ ግራኝ በበኩሉ ፈረሰኞቹም በውስጡና በጉልላቱ ላይ ያለ አሊን ኡስማን ማታንን ልኳቸው መጀመሪያ በውስጡና በጉልላቱ ላይ ያለውን ወርቅና ሀብት ወስደው ቤተ ክርስቲያኑን እንዲቃጠሉት ፤ በ፫ ጉድጓድ የተደበቀም ልብስ አግኝተው እንደወሰዱ እያተተ ፤ ከዚያ ግራኝ ከነጦሩ ከዱ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 206 - 213

ከም ተነሥቶ ወደ ንጉሥ ከተማ ወደ እንዶጥናህ (1) ደርሶ ወታደሮቹ ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው በውስጡ ያለውን በቀይ ፣ በሰማያዊ ፣ በብጫ በልዩ ልዩ ቀለም የተሳለ የአንበሳና የአዕዋፍ ሥዕል እያዩ ከተደነቁ በኋላ እንዲቃጠ ሉት ቃጠሎውን በሩቅ ሆነው የሚመለከቱት ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ቃጠ ሎውን በሚመለከቱበት ጊዜ ከባደቁው ቤተ መንግሥታቸው ይልቅ ለዚህ ኛው ቃጠሎ ከልክ ያለፈ አዝነው "እስላሞቹ እከተማዬ ገብተው መኖሪያ ቤቴን ሲያቃጥሉት ከማየት ለኔ መሞት ይሻለኝ ነበር" ብለው በልቅሶ ለሹማ ምንቶቻቸው መናገራቸውን የዓረቡ ጸሐፊ ይተርካል (2) ።

መቼም በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው የሚገኙትን የከተማ ፡ የመንደር ፣ የቀበሌ ስሞች ዛሬ ከምናውቃቸው ስሞች ጋር አገናዝቦ በትክክል የየአ ንዳንዱን ሥፍራ ለእንባቢ ለማብራራት አስቸጋሪ ነው ። ችግሩንም የፈጠረው ግራኝ አህመድ ከተነሣበት ጊዜ (፲፭፻፲፱ - ፲፭፻፴፩ ዓ.ም.) ዠምሮ በጉንደር መን ግሥት ዘመን ብዙ የተለዋወጠ ነገር በየአውራጃውና በተለይ በዚህ ቀበሌ ስለደረ ሰና የፊተኛውንና የኋለኛውን የሚያሳይ በየዘመኑ የተዘጋጀ ያገር ዝርዝር ካርታ ስለሌለ ነው ።

ለምሳሌ ከግራኝ በፊት አሩሲና በዝቋላ ተራራ ዙሪያ ያለው አገር ማያ በተራ ራው ሥር ያለው ማርዜር ፤ በየረር ዱከም ወንዝ አጠገብ ያለው የንጉሡ ከተማ ባደቄ (ባዶቄ ?) እንጦጦ ቤተ መንግሥታቸው እንዶጥናህ ይባሉ ነበር ማለት ነው ። ይኸንንም የሰየሙት ከጋላ ሥረት በፊት በላዩ ላይ የሚኖሩት የአማራ ክርስ ቲያኖች ወይም ከላዩ ላይ ከጥንት ዠምረው የሚቀመጡት የኩሽ ነገዶች ይሆናሉ ። በኋላ ደግሞ ጋሎች ከግራኝ ወዲህ ከታች ከሱማሌና ከቦረና መጥተው በአገሩ ሲሰ ማሩ በሁሉም ሳይሆን ጉለሌ ቢሾፍቱ አድአ አዳማ እያሉ የአንዳንዱን ስም በቋን ቋቸው ለውጠውት ከጊዜያችን ደርሷል ። በኋላ ደግሞ በሣህለ ሥላሴ ጊዜ የተወጠ ነው የአገር ማቅናት ሥራ ባዬ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ተስፋፍቶ በሸዋ ዙሪያ ያለውን ሁሉ እነራስ ጐበና ሲያቀኑትና አማራ ሲገባበት እንደዚሁ በጋልኛው አጠ ራር ላይ አማርኛ ገብቶ ትንሽ ለውጥ ሊፈጥር ችሏል ። በቅርቡ እንኳን አሁን በዘ መናችን አዳማ ናዝሬት ፤ ቢሾፍቱ ደብረ ዘይት ፤ ወሊሶ ግዮን ፤ አምቦ ሐገረ ሕይ ወት እየተባለ መሰየሙ በጥንቃቄ አሮጌውንና አዲሱን ስም መዝግቦ የሚይዘው የጠፋ እንደሆነ ከአንድ መቶ ወይም ሁለት መቶ ዓመት በኋላ በታሪክ ፊት ሊሳከር ወይም እንዳሁኑ ለማደናገር ይችላል ።

በዓረብ ፋቂህና በሌሎችም የቀድሞ የታሪክ መጻሕፍት ስማቸው የገነነው የደዋሮ የፈጠጋር ታላላቅ አውራጃዎች ዛሬ በፈጠጋር ፈንታ ቡልጋና ምንጃር የረር በደዋሮ ፈንታ አዋሽ ከረዩ አሩሲ ተብለው ተለውጠዋል ። ደዋሮና ፈጠጋር ፈጽሞ

(1) እንዶጥናህ የዛሬው እንጦጦና አዲስ አበባ ያለበት መሆኑ በብዙ ጸሐፊዎች ዘንድ የታመነና የሚ መሰል ነው ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 213 - 215

ስማቸው ባይጠፋም ከታላቅ አውራጃነት ወደ ቀበሌነት ተለውጠዋል ። እምብዛም ስሙ ያልተለወጠው ባሌ (ቀድሞ ባሊ) የዚያን ጊዜ የአውራጃ ወሰኑና የዛሬው ጠቅላይ ግዛት ወሰኑ ለየብቻ ነው ። ስለዚህ ወረራ ያላጠቃው የሰሜንና የምዕራብ ሰሜን ኢትዮጵያ አብዛኛው ጊዜ የስም መለዋወጥ ሳይደርስበት በዚህ የግራኝና ያፄ ልብነ ድንግል ጦር በመገርመሪያዎቹ ዓመቶች (፲፭፻፲፱ - ፴፫ ዓ. ም.) የተቀጣ ቀጡበት አውራጃና ቀበሌ መንደርና ከተማ በትክክል ለማስረዳት በየሥፍራው እየዞሩ ሽማግሌ እየጠየቁ የማጣራቱ ጉዳይ ልዩ ጥናትና ሰፋ ያለ ጊዜ ይፈልጋል ። ነገር ግን የባደቁውን ፣ የሽምብራ ኩሬውን ጦርነት ሲተርክ የዝቋላን ተራራ ፣ የዱከም ወንዝና ሞጆን ስለሚጠቅስ ሁለቱም የጦርነት ሥፍራዎች ከነዚህ ሠፈሮች አይርቁም ። ባደቁው የዛሬው የረር ወይም አጠገቡ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ለመገመት ይቻላል ። እነዚህም ሁሉ የሚገኙበት አውራጃ በጠቅላላው ያን ጊዜ የፈጠጋር አውራጃ ይባል የነበረው አሁን በየረርና በከረዩ አውራጃ ውስጥ መሆኑን እንረዳለን ። ምናልባት የዛሬው ከረዩ ያን ጊዜ የደዋሮ ክፍል ይሆናል ።

የዛሬው የየረርና የከረዩ አውራጃ ግዛት ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ጋር ስለሚገናኝ በዚያን ጊዜ ግን በሁለቱ ይኸውም ማለት በሐረር እንደዚሁ በባሌ መካከል የደዋሮ አውራጃ መገኘቱን አለመዘንጋት ነው ።

በዚህ ምዕራፍ ላይ ዓፄ ልብነ ድንግል ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ ወደ አባቶቻቸው አገር ወደ ቤተ አምሐራ ሄደው ከትግሬም [illegible]ምትም ከአንጎት ከጐጃምም ከበጌምድርም ብዙ ጦር አስከትተው ወደዚሁ ወደ ፈጠጋር እንደገና ተመልሰው በራስ እስላም ሰገድና በትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ አዝማችነት አይፈርስ (ደዋሮ) ላይ አዋግተው አሁንም የግራኝ አሸናፊነት ስለቀጠለ ወደ አማራው አገር ሳይመለሱ በዚያው በፈጠጋር ሆነው አሸናፊው ግራኝ ከነጦሩ ወደፊት እየተጓዘ በዝቋላ በባደቁ በእንዶጥናህ የሚያማምር ቤተ ክርስቲያናቸውን በሥዕል ያጌጠ ቤተ መንግሥትና መኖሪያ ቤታቸውን ሲያቃጥል በሩቅ በሚመለከቱበት ጊዜ ከሁሉ የበለጠ በእንዶጥናህ ያለው መኖሪያ ቤታቸው ያለበት ቤተ መንግሥታቸው ሲቃጠል በሩቅ አይተው "ለኔ ይኸን ከማየት መሞት ይሻለኝ ነበር" ብለው አማረው ማልቀሳቸውን የዓረቡ ጸሐፊ የገለጸው ሐሰት ሊሆን አይችልም ።

ይኸን የመሰለ ያልታሰበ በአባትና በአያት ጊዜ ደርሶና ተሰምቶ የማይታወቅ የጦርነት አደጋና ጥቃት ሲደርስበት ጥቃቱን ለጊዜው የሚመልስበት ሌላ መንገድ ሲያጣ የተናደደ ልብ የቆሰለ አንዠት ለቅሶን ይወልዳል ። እንደዚህ ያለው የለቅሶና የኀዘን መንፈስም ዘውድ የጫኑትንና በዙፋን የተቀመጠውንም ልብ ቢሆን አይምርም ። ብዙ ማንበብ ብዙ ማየትና ማወቅ የሰው ልብ ወደፍልስፍናና ወደ ንቀት ካልተለወጠ በቀር ዘውድ ቢጭንም ባይጭንም ሰው ሲባል ከሥጋ ለባሲነቱ ከደካማነቱ ስለማይዘል ንጉሠ ነገሥቱ በዚያን ጊዜ ያውንጉሣዊ መንፈሳቸው ተዋርዶ ቢያዝኑና ቢያለቅሱ አያስደንቅም ። የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ጣልያን የተረጐመው ማዠር ኤራሲኒ ያህ የእንዶጥናህ የዛሬው እንጦጦ ይሆን ያለውን ሙሴ ረኔ ባሴትም ይመስላል ሲሉ በቍጥር ፩ ማመልከቻ የገለጹት እውነት

ሊሆን ይችላል ። በዚያ ሥፍራ ታሪካዊ ሕንፃ እንደነበረ በንጉሥ ማህለ ሥላሴ ዘመን ወደ ሸዋ የመጡት እነማገርር ሃሪስ ገልጸዋል (1) ።

የእንዶጥናህን ቤተ መንግሥት አቃጠሉ የሚለው ከዝቋላ ወደ ዱከም ወንዝ ከዚያ ወደ ባደቄ (የረር) አልፈው ስለሆነ በእርግጥ ይህ እንዶጥናህ ራሱ እንጦጦ ወይም ከእንጦጦ የማይርቅ በዛሬው አዲስ አበባ አጠገብ የነበረ ከተማ መሆን አለ በት ።

በዚህ መካከል ግን ዓረብ ፋቂህ ይኸንን ሁሉ ከተረከ በኋላ ወዲያው ቀጥሎ ዓፄ ልብነ ድንግል የግራኝ አህመድን ጦር ለመውጋት ቢመጡ የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ አገኙት ስላለ የአዋሽ ወንዝ የሚገኘው ከዝቋላ በደቡብ በኩል እንጂ በዝቋላና በእ ንጦጦ መካከል ስለሌለ ታሪኩን አቃውሶታል ። ምናልባት ውለው አድረው ግራኝ ከነጦሩ እነዚህን አብያተ መንግሥት ከዘረፈ በኋላ ለጊዜው ወደ ኋላው መለስ ብሎ አዋሽን ተሻግሮ ሠፍሮ ሳለ ንጉሡ በቤተ መንግሥታቸው መዘረፍና መቃጠል ተና ደው ለመዋጋት ወደርሱ ሲሄዱ በመካከሉ አዋሽ ሞልቶ ውኂያውን ለጊዜው እግ ዶት ይሆናል ። ወይም ግራኝ እነዚህን ቀበሌ ሲያቃጥል እርሳቸው ከአዋሽ ወደ ደቡብ ወደ ዛሬው ሶዶ ግድም ይሆናሉ ። ከዚያም ሆነው ቃጠሎውን በሩቅ አይተ ውት ወደፊት ገፍተው አዋሽ ደርሰው ይሆናል ።

ISIC

## ምዕራፍ ፵፱

## የራስ ወሰን ሰገድ ከዳሞት መምጣት - ለግራኝ አህመድ የጻፈለት ደብዳቤና የመጣ ለት መልስ (፲፭፻፳፫ ዓ. ም.)

ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱ ጦር ከየአለበት እያስከተቱ የበላይ ይና የበታች እየሾሙ በመላክ ከማዋጋት በቀር ራሳቸው አዝማች ሆነው መዋጋታ ቸውን ታሪከ ነገሥቱም የዓረብ ፋቂህም መጽሐፍ አያወሱም ። አሁንም ወደፊት እንደምናነበው በዚሁ ዓመት በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በሚያዝያ ፲ ቀን ሁለቱ ኃያላን የጦር አለቆቻቸው ራስ እስላም ሰገድና ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ባለፈው ምዕራፍ እንዳነበብነው ከሞቱ ወዲህ ግራኝ ከደዋሮ ወደ ፈጠጋር አልፎ አብያተ ክርስቲያናቱን አብያተ መንግሥቱን ሲዘርፍ ሲያቃጥል ንጉሠ ነገሥቱ ራቅ ባለ ሥፍራ ሆነው ቃጠሎውን እያዩ ማዘናቸውን ገልጾ የዓረቡ ጸሐፊ ዳሞት ወደሚገ ኘው ወደ ራስ ወሰን ሰገድ ይፋት ወደሚገኘው ወደ እውራይ ኡስማን እንዲደርሱላ ቸው መላካቸውን ከአስገነዘበ በኋላ ራሳቸው የነዚያን መምጣት ሳይጠብቁ በአጠ ገባቸው ያለውን ጦር እንደያዙ ወደ ግራኝ መሄዳቸውንና በሁለቱ ባላጋራዎች መካ ከል የሞላው አዋሽ ውኂያውን ስለከለከላቸው የሁለቱም ወገን ተዋጊ ጦር ማዶ ለማዶ እየተያየ ይሰዳደብ እንደነበረ ይገልጻል ። ከዚሁ አያይዞ እንግዲህ ወኃው

(1) Highland of Ethiopia ፪ኛው ቶም ገጽ 178 - 200

ሞልቶ ከላሻገረንና ካልተዋጋን ወደ በረራህ እንሂድ ብለው ከነሠራዊታቸው መን
ዛቸውን ግራኝም ስንቅ በያለበት እንዲሰበሰብ ገራድ ጁሻህ የሚባለውን ልኮት
ወታደር አስከትሎ ሲሄድ በራራህ (በረህ ?) ከሚባለው አገር ላዩን ሲያልፍ ዓፄ
ናዖድ ወደ አሠሩት ቤተ ክርስቲያን ሳያስበው ደርሶ ከነወታደሮቹ በውስጡ ሲገቡ
ወርቅ ሞልቶበት እንደ አገኙ የነርሱም አሳብ የሥጋ ከብት ሰብስበው ወደ ጌታ
ቸው ለመመለስ እንጂ ይኸን የመሰለ ሀብት እናገኛለን ብለው ሳይጠረጥሩ በዚህ
ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የበረከተ ወርቅ በወርቅና በብር የተሠራ ሰንና ብርት በያይ
ነቱ ልብስ ስላገኙ ደስ ብሏቸው ያንን ሰብስበው ወደ ግራኝ ተመልሰው ሄደው
በዚህ በበረህና በዙሪያው የሚገኘውን የወርቅና የገንዘብ ብዛት እንደነገሩት . . . .
ኰተረከ በኋላ ዓረብ ፋቂህ ስለግራኝ አህመድ መታመምና ስለራስ ወሰን ሰገድ ከዳ
ሞት መምጣት በሰፊው ያትታል ።

ራስ ወሰን ሰገድ ከዓፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ዠምሮ በቤተ መንግሥቱ የተ
ከበረ በሕዝብ ዘንድ የተወደደ የደሃ አባት የሚል ስያሜ የወጣለት ታላቅ ሰው
ነው ። በቤተ መንግሥቱ ደረጃው ፪ኛ ምክሩና ተሰሚነቱ ከሌሎች ሊቃውንትና
አዋቂዎች የበለጠ መሆኑን እንደ ንግሥት እሌኒና እንደ ንጉሡ እናት እንደ ናዖድ
ሞገሳ ዋና የመንግሥቱ ሁለተኛ ደረጃ ያለው ደጋፊ መሆኑን የልብነ ድንግል ዜና
መዋዕል ይገልጻል (1) ።

በቤተ መንግሥቱ የሹማምንቱን ደረጃ የሚያሳISICርዝር በጽሑፍ ማስፈር
በዚህ ዘመን ስለአልተለመደ ትክክለኛውን አናውቀውም ። ይሁን እንጂ ከዚህ
በፊት እንዳልነው ከንጉሡ የሚከተለው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ሲሆን ከሁሉም
መኳንንት ራስ ወሰን ሰገድ ቀድሞ ከነገደ ኢየሱስ ቀጥሎ በመንግሥቱ ደረጃው ፪ኛ
ነው ማለት ነው ። ሁለት የግራና የቀኝ ቢትወደዶች መሾም ልማድ ስለነበረ ራስ
ወሰን ሰገድ የግራ ቢትወደድነትን በያዘበት ጊዜ የቀኙ ራስ እስላም ሰገድ ቢትወ
ደድ ሠርጼ የግራውን በያዘበት ጊዜ እነራስ ነቢያት የቀኙን ይዘው ስለነበረና ከቀ
ኙም የግራው ስለሚበልጥ ራስ ወሰን ሰገድና ቢትወደድ ሠርጼ የሹመት ደረጃቸው
ይመጣጠናል ። ነገር ግን ባንደኛው የገበዘ አክሱም ጽሑፍ ውስጥ የራስ ዓምዱ
ልጅ ሠርጼ አዛዥ በነበረበት ሰዓት ራስ ወሰን ሰገድ የግራ ቢትወደድ ስለነበረ በዚ
ህም ላይ ዕድሜውም የገፋ ስለሚመስል ከሁሉም ደረጃውና ማዕርጉ የርሱ ይበል
ጣል ማለት ነው (2) ። አሁንም ከዳሞት መጥቶ ሹማምንቱን ሲወቅስ አነጋገሩና
ተዋጊው ሠራዊት በእርሱ ላይ እምነት መጣሉ ሲታይ የቀረው ቢቀር በአሁኑ
ሰዓት የሁሉም በላይ መሆኑ ይታወቃል ።

በፊት ጐጃምን ገዝቷል ፤ በአሁኑ ሰዓት ዋና ግዛቱ ዳሞት ነው ። ዳሞት ሲባ

(1) ወእማዝ ትትሚገብ መንግሥት በትእዛዘ ወላዲቱ ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ወበካልእታ ንግሥት
እሌኒ . . . ወበምክረ ኵሎሙ ዓበይተ ቤተ መንግሥት ማእምራን ወጠቢባን ወፈድፋደሰ በም
ክረ ጠቢብ ወለባዊ ወሰን ሰገድ በዓለ ዳግም መዓርገ መንግሥት . . . ያቄ ልብነ ድንግል ታሪክ
ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 6 ።
(2) መጽሐፈ አክሱም ገጽ 29 - 30

ልም የትኛው መሆኑን ባሁኑ የጦርነት ሰዓት እስከትሏቸው የመጡት አገሬዎች
ያስረዱናል ። እነሱም ጉራጌ ፤ ጋፋት ፤ ዳሞት ራሱ እናርያ ኤዝ (ዘይት ?) ጅማ የሚ
ባሉት ናቸው ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ድረስ
በብዙ ቦታ ሲዋጋ የራስ ወሰን ሰገድ መዋጋት በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ አይገኝም ።
ከአይፈርስና ከዛሬ ጦርነት በኋላ በዝቋላና በዱከም አካባቢ የሚገኘው አብያተ
መንግሥትና አብያተ ክርስቲያናት የተዘረፈና የተቃጠለ ጊዜ ንጉሡ ነገሥቱ ልብ
ውበት ከዳሞት ብዙ ጦር ይዞ ደረሰ ። እንደደረሰም ከናንተ በፊት አባቶቻችሁ አያ
ቶቻችሁ ያሸንፏቸው የነበሩት እስላሞች እንዴት አሸነፏችሁ ? በአባቶቻችሁ ጊዜ
ያልደረሰው ይህ መከራና ውርደት በናንተ መድረሱ ሕዝቡን ያለፍርድ በመበደላ
ችሁ እነዚህን እስላሞች አስነሥቶ አሸነፏችሁ ብሎ በጋለ ንግግር መውቀሱ ለጥ
ቂት ጊዜም ቢሆን ከመንግሥቱ አስተዳደር ባለመስማማት ገለል ብሎ የኖረ ይመ
ስላል ። የሆነ ሆኖ አሁን ሹማምንቱ ሁሉ እየተላቀሱ አዳምጠው እስካሁን የምን
ጠብቀው አንተን ነበር እንግዲህ ከእስላሞቹ ጋር አፊትህ እየተዋጋን እንሞታለን
ብለው ኀዘንና ጸጸት በተደባለቀበት ፉከራ ገለጹለት ።

ከዚያ ጦርነቱን ከመዠመሩ በፊት ባንድ ወገን ለጦርነት እየተዘጋጀ በሌላው
ወገን ለግራኝ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንደዚህ ሲል ጻፈለት «. . . . . እናንተ እስላ
ሞች እኛ ክርስቲያኖች ንን ከዚህ በፊት በአገራችሁ ላይ እየዘመትን አገራችሁን
ዘርፈን ቤታችሁን አቃጥለን ነበር ። አሁን ግን እግዚአብሔር አሸናፊነትን ሰጣችሁ ።
ነገር ግን አሸናፊነት ሁልጊዜ አይገኝም ፤ እስካሁን ያደረግኸው ይበቃሃልና ወዳገ
ርህ ተመለስ ። መቼም በሽምብራ ኲሬ ንጉሡን አሸንፌ አባርሬአለሁ ፤ በአንጾኪያ
(አይፈርስ) በዛሬ የንጉሡን ጦር ጨርሻለሁ ብለህ መመካትህ አይቀርም ። ነገር ግን
አታብዛው . . . . . የንጉሡ ጦር እንደቀድሞው ተቋቁሟል ። ከርሱም ጋር ከዚህ
ቀደም አይተኸውም ሰምተኸውም የማታውቅ የጉራጌ ፣ የጋፋት ፣ የዳሞት ፣ የእና
ርያ የኤገዘ ዘይት (በጐጃምና በወለጋ መካከል ያለ ?) የጅማና እነሱን የመሳሰሉት
አገሮች የንጉሡ አገልጋዮች ከሆኑት ጋር አብረው አሉ ። ስለዚህ እስካሁን የሰ
በሰብኸውን ምርኮና ወርቅ ይዘህ ወደ አገርህ ተመለስ ። እምቢ ካልህ ቅዳሜ እንገ
ናኛለን ። ካንተ በዕድሜ የሚበልጠውን ወንድምህን ገራድ አቡንን የኢብራሂምን
ልጅ የገደልሁ እኔ ነኝ ፤ ጦሩን ብዙ ጊዜ በታትኜ ያባረርሁ እኔ ነኝ ፤ እስካሁን እንደ
ተዋጋሃቸው ያሉ ሹማምንት እንዳልመሰልህ እኔ ወሰን ሰገድ ነኝ ።»

ስለዚህ ጉዳይ ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ይተርካል ። «ይኸን ጽፎ ሰጥቶ የላ
ከው መላክተኛ እወዚር አዶሌ ዘንድ መጣ ። በዚህ ጊዜ ይማም ታሞ ተኝቶ ነበር
ወዚር አዶሌ ወደርሱ ሄዶ ነገሩን ሁሉ ነገረውና «እንዴት ማድረግ ይሻላል መላከ
ተኛው እንደዚህ ታመህ መተኛትህን ያየ እንደሆነ ለጓደኞቹ ተመልሶ ነግሮ ልባቸ
ውን መልሶ ያጠነክረዋል» አለ ፤ በዚያ ከነበሩት አንዱ «ያጐትህ ልጅ ዘሀርቡይ
መሐመድ ባንተ ፈንታ ይቀመጥና መላክተኛው ሲመጣ ይማም ይኸውልህ እንለ
ዋለን» ብሎ ቢናገር የቀሩት «ይኸ ጥሩ ምክር አይደለም ከክርስቲያኖቹ አብዛኞቹ

ማምን ያውቁታል ። መላክተኛውም ወደነሱ ተመልሶ ይማምን አግኝቼ አነጋገር
ት ሲላቸው ምን መሳይ ነው ማለታቸው አይቀርም ፤ እርሱም ይኸን ይመስላል
ሉ የዘሀርቡይን መልክ የገለጸላቸው እንደሆነ የሁለታችሁን የመልክ ልዩነት
ሚያውቀት ይማም ስለሞተ በርሱ ፈንታ የሚመስለውን ሰው አስቀምጠው አነጋ
ሩ ይላልና ይኸኛው ደኅና ምክር አይደለም ፤ ይልቅስ ይማም ልብሱን ይልበስና
ርትቶ ይቀመጥ ፤ መላክተኛውም ገብቶ ያነጋግረው ብለው ይማምም የተሻለው
ምክር የናንተ ነው አላቸው ።

በማግሥቱ የእስላሞቹ ጦር ፈረሱን ጭኖ የጦር መሣሪያውንና ጋሻውን ይዞ
ተሰልፎ እንደቆመ መላክተኛው ገባና ደብዳቤውን ለይማም አቀረበለት ። ይማ
ምም በደብዳቤው ላይ ያለውን ከተገነዘበ በኋላ ነገሩን ለጓደኞቹ አስረዳቸው ። በዚ
ያን ጊዜ ከእስላሞቹ ሹማምንት አንዱ በለው አብዱ የሚባለው ለመላክተኛው
"ሂድና ለጌታህ እንደዚህ በለው እነዚህ ይዋጋሉ ያልካቸውን የዳሞትና የጉራጌ
ሰዎች ችሎታቸውን እናውቀዋለን ፤ እነሱም ሥራቸው እርሻ ከዚያ ደግሞ ዛፍ እየ
ቈረጡ ወደኛ አገር ከማመላለስ በቀር ጦርነት ምን መሆኑን በፍጹም አይተው አያ
ውቁምና በምናውቃቸው ባሮች በፍጹም አታስፈራራን አንተ ግን እንደምትለው
ጉበዝ ከሆንህ በመሬትህና ባገርህ ላይ ነንና ተዋጋን ብለህ ንገረው" አለው ። እር
ሱም ሲጨርስ አሚር ሑሴን የሚባለው ተነስቶ "ቅዳሜ እንጥማችኋለሁ ያልኸ
ውን በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ፈቃድ አንተ እንደም[illegible] ሼኮቻችን አረጋግጠ
ውልናል በለው" አለ ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ግራኝ አህመድ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የመጨረሻ ቃል
ነግሮ መላክተኛውን አሰናበተው "እስከመጨረሻው ድረስ አለበት ድረስ እንደም
ናባርረው ለጌታህ ንገረው ። ወደ አገራችሁ ተመለሱ ያለውንም አንሰማማበትም ።
ጦርነቱን ለማድረግ ፈቃዳችንና ፍላጐታችን ነው ። ነገር ግን የሚዋጋን ሰው አላገ
ኘንም ። እስካሁንም የያዝነውን አገር በመልቀቅ ፈንታ በእግዚአብሔር ፈቃድ
ነቢዩ መሬት ለኔ ተጠቀለለች ፤ ምሥራቅና ምዕራብንም አየሁ ወገኔ ዓይኔ ያየውን
ሁሉ ይገዛል ብሎ ተስፋ እንደሰጠን ሀበሻን በሙሉ እንገዛለን ።"
መላክተኛው ይኸን ሁሉ ቃል ከሰማ በኋላ ከግራኝ አህመድ ዘንድ ተመልሶ
መልእክቱን ለራስ ወሰን ሰገድ ነገረው» (1) ።

በዚህ ምዕራፍ ላይ በተመለከትነው ውስጥ የአንድ ግብጻዊ ጳጳስ ቤተ ክርስቲ
ያን አግኝተው እስላሞቹ ዘርፈው እንዳቃጠሏት ከገለጸ በኋላ ራስ ወሰን ሰገድ ለመ
ላንንቱ የወቀሳ ዲስኩር ባደረገበት ላይ . . . . . አባታችሁን ፓትሪያርኩን (ጳጳ
ሱን) ከነቤተ ክርስቲያኑ እስላሞቹ አቃጠሏቸው ማለቱን አንብበናል ። በዚህ ጊዜ
የነበሩት ግብጻዊው ጳጳስ ባለፈው የጠቀስናቸው አቡነ ማርቆስ ናቸው ። የዓ
ረቡ ጸሐፊ ፓትሪያርክ የሚላቸው ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ጋር እየተማታ
በት ነው እንጂ እርሳቸው የኢትዮጵያ ጳጳስ ስለሆኑ የፓትርያርክነት ማዕርግ የላቸ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 216 - 231

ውም ። አልቫሬጽ ከዶም ሮድሪግ ጋር እ  አ  ቆ  በ፲፭፻፲፪ ዓ ም  መጥቶ በ፲፭፻፲፰ ዓ. ም. እስኪመለስ ድረስ ስድስት ዓመት በኢትዮጵያ በነበረ ጊዜ ብዙ ጊዜ ጳጳሱን እንዳነጋገራቸውና ዕድሜያቸው በዚያ ሰዓት ከመቶ ሃያ በላይ እንደነበረ ፤ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሥራው አልቆ በተመረቀ ጊዜ ያዩ ናዖድ  አጽም ወደዚሁ ወዳዲሱ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ጳጳሱ በጣም ከመድከማቸው የተነሣ ሁለት ሰዎች ግራና ቀኝ ደግፈዋቸው በዓሉን እንደተካፈሉ አረጋግጧል (1) ።

አሁን እኚሁ ጳጳስ አቡነ ማርቆስ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. የሽምብራ ኩሬ ጦርነት በተደረገ ባመቱ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ምሕረት ሞተዋል (2) ። የተቀበሩትም በዚሁ ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን ኖሮ አሁን በሞቱ በሁለተኛው ዓመት በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. እስላሞቹ ከነአጽማቸው ቤተ ክርስቲያኑን አቃጥለውታል ማለት ነው ።

ራስ ወሰን ሰገድ እምቢ ካልህ ቅዳሜ እንገናኛለን ብሎ የጻፈውን ምናልባት ወሰን ሰገድ ይኸን ቀን የመረጠበት ምክንያት መነኩሴዎች በዚህ ቀን ታሸንፋለህ ብለው ነግረውት ይሆናል ። ለዚህም በበኩላቸው የተዋጊውን መንፈስ ተስፋ ለማ ስቆረጥእስላሞቹበዚህቀን በኛእጅእንደምትሞትየኛ ሸኾችአረጋግጠውልናል ፤ እንደዚሁም ይዘኻቸው የመጣኸው ወታደሮች (ጉራጌ ጋፋት) ከርሻና ከእንጨት ቆረጣ በቀር ጦርነት አያውቁምና በከንቱ አታስፈራራን ያሉት በአጠገባቸው ካሉት ውስጥ እንደነበረው እንደ በለው አብዱ ያሉት ውስጥ አወቅ ናቸው ማለት ነው ። ያለነው በመሬት[illegible]ይ ነውና ይልቅስ ናና ተዋጋን ማለታቸውም ሁሉ በፍ ጹም ጉብልታቸውን እንደተማመኑት ያስረዳል ።

በተረፈ ራስ ወሰን ሰገድና ግራኝ አህመድ የተመላለሱትን ቃላት ስናመዛዝን ግራኝ በሙሉ ልብ ኢትዮጵያን ለመውረርና ለመግዛት በያዘው አዳዲስ መሣሪያ በተከተለው ወታደር ከዚያም ከሁሉ የበለጠ በራሱ ተማምኖ የተነሣ መሆኑን ስንገ ነዘብ "የሚዋጋን አጣን" በሚል የአብሪት ቃል ጨምሮ መልከተኛውን መልሶ ሲልክ በእርግጥ ጊዜውም የጦርነቱም ዕድል ለርሱ እንዳደላለት አውቆታል ማለት ነው ።

ራስ ወሰን ሰገድ በበኩሉ ድል ሁል ጊዜ አይገኝምና እንግዲህ እስካሁን የዘረ ፍኸው ይበቃሃልና ምርኮህንና ወርቅህን ይዘህ ወዳገርህ ግባ እምቢ ካልህ ቅዳሜ እንገናኛለን ማለቱ በእርግጥ ጊዜው ያደላው ለግራኝ መሆኑን ከመገንዘብ ጋር በራ ሱና በተከተለው ጦር በሙሉ እንዳልተማመነ ያስረዳል ። ያለዚያ ወዳገርህ በሰላም ግባ ብሎ የዛቻ ስንብት በመላክ ፈንታ መጣሁ ጠብቀኝ ብሎ ግራኝ ጦርነቱ ከተዠ መረ አንሥቶ በአራት ዓመት ውስጥ በደዋሮ ፤ በሽምብራ ኩሬ ፤ በአይፈርስ በአገ ራቱ ላይ ያደረገውን እልቂትና ጥፋት ብድሩን መመለስ በተገባው ። በዚህ ፈንታ ወደ አገርህ ግባ ብሎ ይኸን ሁሉ ጥፋት ባገር ላይ ያመጣውን ባላጋራ በምክር ለማ ሰናበት መሞከር ስለድሉ ያለው እምነት ያነሰ መሆኑን ያሳያል ። ከደብዳቤውም

(1) Verdadeira  አልቫሬጽ . .. . . ምዕ. 100

(2) Liber Axum-Conti-Rossini "ዘታሪክ ወፍትሕ" ገጽ 68

መለዋወጥ በኋላ የተደረገው ጦርነት በዚያው በተለመደው የግራኝ ድል አድራጊ
ነት ላይ ሌላ ድል አድራጊነት በመጨመር ቀጠለ እንጂ የደብዳቤው ዛቻ ምንም
ረብ አላመጣም ።

## ምዕራፍ ፱

## የራስ ወሰን ሰገድ ፕላን - የዝሆንዱር ጦርነት - የዓምደ ሚካኤል አሟሟት (፲፭፻፳፰ ዓ.ም.) ።

ራስ ወሰን ሰገድና ግራኝ አህመድ የዛቻቸውን መልእክት ከተለዋወጡ በኋላ ግራኝ
ከሕመሙ መዳኑን ዓረብ ፋቂህ ይገልጽልናል ። የዳነበትን ጊዜ በእስላሞቹ አቈጣ
ጠር ፳፫ ራማዳን ፱፻፴፯ ያደረገውን ሙሴ ረኔ ባሴት የውስቲንፊልድን (Wasten-
Feld) አቈጣጠር መሠረት አድርገው እ.አው.አ. ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፭፻፴፩ ዓ. ም.
ያደረጉት በኛ ያው ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ግንቦት ፫ ቀን ይሆናል ።
የሆነ ሆኖ ግራኝ ድኖ ከተነሣና የለመደውንና የሚወደውን ጦርነት መከታተ
ሉን ከመጀመሩ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግልና ራስ ወሰን ሰገድ ቀደም
ብለው ተገናኝተው ሲመካከሩ ሰንብተው እንደነበሩ አሁን የግራኝ ጦር ከበረህ (1)
መንቀሳቀሱን ሲሰሙ ወሰን ሰገድ አንድ የጦርነት አሳብ (ፕላን) በመፍጠር ለን
ጉሠ ነገሥቱ እንደዚህ እንደ አላቸው የዓረቡ ጸሐፊ ያመለክታል ። «አሁን እስላ
ሞቹ ያሉት በኋላችን ነው ። ሁላችንም ወደ ዳሞት የሄድን እንደሆነ አገሩ ጠባብ
ስለሆነ ተከታትለው ሊያስቸግሩን ይችላሉ ። ስለዚህ እርስዎ ወደ ዳሞት ይሂዱ ። እኔ
ግን በእስላሞቹ ኋላ አድርጌ ወደ አገራቸው (ወደ ሐረር) እጓዛለሁ ። ይኸንንም ሲያ
ውቁ ተመልሰው ወደ አገራቸው ይሄዳሉ ። እስከ ደዋሮ ድረስ ከአስጓዙዋቸው
በኋላ ከዚያ ወዲያ ተበታትነው ወደየ ክፍለ አገራቸው መግባታቸው አይቀርምና
እኔም ተመልሼ ወደርስዎ እመጣለሁ»
ከዚሁ እያይዞ ዓረብ ፋቂህ ንጉሠ ነገሥቱ በዚሁ አሳብ ተስማምተው ወደ
ዳሞት ሲሄዱ ራስ ወሰን ሰገድም እንዳለው ወደ ደዋሮ አቅጣጫ መምራት ሲዠ
ምር የግራኝ አህመድ ሰላዮች መጥተው የራስ ወሰን ሰገድን የጦርነት ብልሃት እን
ደገለጡለት ያረጋግጣል ። በዚህ ምክንያት ግራኝ የራስ ወሰን ሰገድን የጦርነት ዘዴ
ለማጨናገፍ የሀበሻን አገር መንገድ በሙሉ አውቃለሁ የወረባንም የዳሞትንም
የጕጃምንም መንገድ እስከ አክሱም ድረስ ወደፈቀዳችሁበት ሥፍራ ልመራችሁ
እችላለሁ ብሎ በፎከረለትና በዚሁ በሸለመው ባንድ በቅርብ ቀን ሰልሞ ከርሱ ጋር
በነበረ ከዳተኛ እየተመራ ወደ ዳሞት የንጉሡን ዱካ እየተከታተለ ገሠገሠ ። የራስ
ወሰን ሰገድ አሳብ ወደ ሐረር በመጓዝ ግራኝን ከነጦሩ ለመሳብ ሲሆን የግራኝ አሳብ

(1) ዓረብ ፋቂህ ይኸን ሥፍራ ፩ ጊዜ በረረህ (በርረህ ?) ሌላ ጊዜ በረህ ስለሚለው እውነተኛ ስሙ
ይሀ የመጨረሻው ሳይሆን አይቀርም ። እርሱም ከአዲስ አበባ ሄዶ ሰንዳፋ ሲደርስ ወደግራ ያለው
ተራራማ ሥፍራ ይሆን ?

ደግሞ ገሥግሦ ሄዶ ንጉሡን አጣድፎ በመውጋት ወሰን ሰገድ ሳይርቅ ይኸንኑ ሰምቶ ንጉሡን ለመርዳት እንዲመለስ ነው ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድና ሠራዊቱ ከወበራ ወደ ኡይዝ ፥ ከኡይዝ ወደ ቆብ ፥ ከቆብ ወደ ምስር ምሽግ ወደሚባለው ደረሱ ። ሥፍራው ጠባብና ጫካ ከመሆኑ የተነሣ በግራኝ አህመድ ትእዛዝ ወታደሩ ድንጋዩን እየሰባበረ ጫካውን እየመነጠረ አልፎ ሌሊቱን ሱቅ ወይዘሮ ወደሚባለው ሠፈር ደረሰ ። ንጉሡ ነገሥቱ የእስላሞቹን ዳሞት መግባት ሲሰሙ ጦራቸውን ዝሆን ዱር በሚባለው በተራራው ጐን አሰልፈው አስቀመጡና እርሳቸው ወደ ከፍተኛው ተራራ ወጥተው ተቀመጡ ። ወደዚያም የሚያስሄደው ጀርጂ (ጎራጌ ?) የሚባለው ዋነኛ በር አንድ ብቻ ነበር ።

ዓረብ ፋቂህ ግራኝ ከነጦሩ ወደዚሁ ወደ ተራራው ከተጠጋ በኋላ በእንዴት ያለ አኳኋን የንጉሡ ጦር ወዳለበት ወደ ዝሆን ዱር ደርሶ እንደምን እንደተዋጋ በቀጥታ በራሱ አነጋገር የሚለውን እንመልከት ።

«እስላሞቹ ከሱቅ ወይዘሮ ተነሥተው ወደ ጀርጂ ሰፈሩና ከክርስቲያኖቹ ጋር ይሰላለሉ ጀመር ። ክርስቲያኖቹ በላይ በኩል መሥፈራቸውን ባወቁ ጊዜ እስላሞቹ ምክር ያዙ ። አዶሌና በለው አብድ ከጓደኞቻቸው ጋር ከፊታችን በሩ ተይዞብናል ከዚህም በቀር ሌላ መሄጃ መንገድ የለም እዚሁ ሌሊቱን እናሳልፍና በመድፍ እየተኰስን መትተን ነገ ጧት ውጊያውን እንጀምር አሉ ። አሚር ዘሀርቡይ መሐመድ ፤ አብድ ኢ[illegible]ርና ገራድ አህሙሹ ግን እዚህ ሌሊቱን ያደርን እንደሆነ ከኋላችን (ወሰን ሰገድ) መጥቶ የምስር ምሽግን በር ይይዝብናል ይኸም ሲሆን ወደ ተራራ መውጣት ወይም መመለስ ሳንችል በሁለት ተራራ መካከል እንቀራለን ።

ስለዚህ ድሉን እግዚአብሔር እይነሣንምና ውጊያውን አሁኑኑ እንጀምር ብለው መለሱ ። ይማም አህመድም አሁን መልካም ምክር አመጣችሁ ብሎ ጦሩን ለውጊያ አሰለፈና አውራይ ኡስማን ወደሚጠብቀው በር ተጠጋ ከዚያ በበሩ በኩል ጦሩን ይዞ እንዲጠባበቅ ወዚር አዶሌን ተወና ይማም የራሱን ጦር ይዞ ወደ ዝሆን ዱር ሄደ ። ንጉሡ በዚህ በጠባብና ማንም በማያውቀው መንገድ እስላሞቹ ይመጣሉ ብሎ አልጠረጠረም ነበር ፤ ሁሉም ሰው ወደ ዝሆን ዱር ማንም ሊወጣ አይችልም እያለ አረጋግጦለት ነበር ።

ይማም ከነሰዉ ወደ ዝሆን ዱር ሲደርስ በዛፍና በእሾህ የተዘጋ ፫ በር አገኘ ። በዚያን ጊዜ ሻምሱ ለሚያዛቸው ለእግረኛ ወታደሮች ጋሻችሁን እሾሁ ላይ እያስቀመጣችሁ እርሱን እየረገጣችሁ ግቡ ብሎ አዘዘና እርሱ እንዳለው ጋሻቸውን እየረገጡ አልፈው ሊተነፍሱ ወደ ቻሉበት ሥፍራ ገብተው አጥሩን አነሡና ይማም ከነጦሩ አብሮ ገባ ፤ ንጉሡም እስላሞቹ ሳይቀድሟችሁ ሂዱና በሩን ያዙ ብሎ ለትግሬ ጦር አዝዞ ነበርና ቢመጡ እስላሞቹ ቀድመው ይዘውት ደረሱ ። ቢሆንም እዚያው እጠገብ እጠባብ ሥፍራ እንዳሉ እስላሞቹ እዩዋቸውና ሼክ ሚካኤል ሱማሌው ማታን ፤ ሲዲ ሞሐመድ ፥ አብድ ኢን ናስር ፥ አውራይ አቡን ፥ አሚር አቡበከር ፤ አውራይ ኡስማን ቢን ዓሊ ፥ ከቢር ሞሐመድ ሌሎቹም በድምሩ አርባ

የሚሆኑ ፈረሰኞች በፊታቸው ያለችውን ትንሽ ሸለቆ አልፈው ከክርስቲያኖቹ ጋር ኃይለኛውን ውጊያ ዠመሩ ። ተክሉ የሚባለው የሠራዊቱ ሹም (ክርስቲያን) ገሥግሦ መጣና ሼክ ሚካኤልን በጦሩ ቢመታው የጦሩ ጫፍ አጥንቱን ሰብሮ እግሩን ቀዶት ወጣና ይታይ ዠመር፤ ቁስለኛውም ከሁለት ቀን በኋላ ሞተ. . . . . ። አባቱ ሮቤል በሽምብራ ኩሬ ጦርነት የሞተው ዓምደ ሚካኤል (ዓምዱ) እንደዚሁ አቡበክር ቀጢንን ገጥሞ በጦር ሲደባደቡ ዓምዱ በጦሩ አቡበከር የተቀመጠበትን የፈረሱን አንገት ቢወጋው የጦሩ ጫፍ ባንድ ወገን ብቅ አለ ። ከዚያ ላይ ጦሩን ነቅሎ የአቡበክርን ቀኝ ቅልጥም መታው ። አቡበክር ቀጢንም በጦሩ ዓምዱን ልቡን ቢለው የጦሩ ጫፍ በዠርባው ታየና ከፈረሱ ላይ ወደቀ ። ቢሆንም የጦሩ በትር ቢያመውም ከአቡበክር ጋር ተጨባብጠው ሲደባደቡ የዓምዱ ዘመድ ረዳውና አቡበክርን ዠርባውን ሲመታ አብድ ኢን ናስር ደግሞ ክርስቲያኑን (ረዳቱን) መታና ከፈረሱ ጥሎ ገደለው ። ዓምዱም አቡበክር በወጋው ጦር ሞተ . . . . . ። ጓደኞቻቸው በዚህ ዓይነት ሲሞቱ የቀሩት ክርስቲያኖች ሸሽት ዠመሩ ። እስላሞቹም እየተከታተሉ ገደሏቸው ። ሼክ ሚካኤልን የገደለውን ተክላይን የሠራዊን ሹም አውራይ አቡን ማረከው ። የሾጃራህን ሹም የገራድ ሲዲቅ ጋሻ ዣግሬ ማረከው ። ከእስላሞቹ አንድ ብቻ ሲሞት የትግሬ ሹማምንት ስምንት ሞቱ ። ፰ ፈረሰኞችም ተማረኩ ዋናው አዝማች ዮናኤል የተረፈውን ጦር ይዞ ወደ ንጉሡ ሄዶ እስላሞቹ በሩን አልፈው ያደረጉትን ሁሉ ነገረው ። ንጉሡም በሰማ ጊዜ ዓምደ ሚካኤል የሮቤል ልጅ ሞተ ! ብሎ ጮኸ ። ምክንያቱም ዓምደ ሚካኤል ያባቱን የሮቤልን ማዕርግና ደረጃ ይዞ ትልቅ ሰው ዠግና ተዋጊነቱም በክርስቲያኖች ዘንድ የታወቀ ስለነበረ ነው ። አባቱ ሮቤል እፊቱ የሚዋጉለት ፭፻፶ የሚሆኑ የኑብያ የፈረሰኛ ባሮች ነበሩት ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ የዳሞትን ግዛት ለቀው ወደ ወጅ ሄዱ ። አውራይ ኡስማንም የንጉሡን መሄድ ሲሰማ የጀራጂን በር መጠበቁን ትቶ ወደ ንጉሡ ሄደ ። እሱን ይጠባበቅ የነበረው ወዚር አዶሊም ወደ ዝሆን ዱር መጥቶ ከይማም ጋር ተገናኙና ባንድነት ሆነው ንጉሡን ይከታተሉ ዠመር ።

ይህ ጊዜ የበልግ ወራት ነው ። በዚህም ወራት ሀበሾች አራት ወር ክረምት በቤታቸው መቀመጥ ልማድ ነበራቸው ። ነገር ግን አሁን ብርድና ዝናም በበረከተበት ጊዜ እስላሞቹ ንጉሡን ሲያባርሩ የዝናቡ ብዛት መሬቱን ሁሉ ጭቃ አደረገው ። መድፎቹንም መጣል አስፈለገ ። እስላሞቹ ሰባት ነበራቸው ከክርስቲያኖቹ ላይ የማረኩት አሥር ነበርና ከድካም የተነሣ አሥሩ ሰባቱን መድፍና የተማረከውን ድንኳን ሁሉ ከድካምና ከችግር ከመንገዱም መጥፎነት የተነሣ ተጣለ ። ከዚያ እስላሞቹ ንጉሡን እያባረሩ ኡኢሀ - ያሀር እምትባል ከተማ አደረሱት ። ክርስቲያኖቹ በዚች ከተማ በደረሱ ጊዜ የዝናምና የብርድ ብዛት ከመካከላቸው ፫፻ ሰው ገደለ ።

ክርስቲያኖቹ በብርድ መሞታቸውን ሲሰማ ይማም ወደዚች አገር መሄዱን አቆመ ። ንጉሡ ግን በዚች ከተማ ሳያድር ወደፊት ገሥግሦ ወደ ገበርጌ ምድር

ደረሰ ። ወሰን ሰገድም ወጅ ነበረና ከዚያ ወደ ገበርጊ መጥቶ ከንጉሡ ተገናኘ ። ንጉሡም በዝሆን ዱር የተደረገውን ጦርነትና መሸነፍ አጫወተው ወሰን ሰገድም በንጉሡ ፊት የጦር ሹማምንቱን እንደዚህ ሲል ወቀሰ ።

“እንዴት ብታደርጉ ይህ ደረሰ ? በውነት ሰነፋችኋል ። የዳሞት ግዛት ተራራ የሞላበት መንገዱ ጠባብ ሳለ በሩን ይዛችሁ በመከላከል ፈንታ እስላሞቹ እያባረሯችሁ አገሩን ትታችሁ ሸሻችሁ ፤ ሞትን ትፈራላችሁ አባቶቻችሁ እያቶቻችሁ ስለ ሃይማኖታቸው ከመሞት በቀር ይኸን የመሰለ ውርደት ደርሶባቸው አያውቅም ። አሁን እናንተ ደግ መስሎ የታያችሁን አድርጉ ፤ እኔ ግን ስለሃይማኖቴ ተዋግቼ እሞታለሁ” (1) ።

ይኸን ተናግሮ ሲጨርስ የጦር አለቆቹ “አንተ ከሞትህ ሃይማኖታችንም መሞቱ ነውና ሞት አያድርስብህ አንተም መሪያችን ነህና እሞታለሁ አትበል” ሲሉ መለሱለት ።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ብዙ ነው ።

፩ኛ ራስ ወሰን ሰገድ ለንጉሡ ያቀረበውን የጦርነት አሳብ መስማት እስኪችሉ ድረስ የግራኝ ሰላዮች በንጉሡና በየጦር አለቆቹ መካከል መገኘታቸውን ከነርሱ ባገኘው የወሬ ምንጭ ግራኝ ከዚህ በፊት እንዳልነው ንጉሡን በጥድፊያ አባሮ በመውጋት ፕላኑን እንዳፈረሰባቸው ። በዚህም ላይ አገሩ ለጥብሎ ሊገዛ የሚችለው አውራውን ንጉሥ በመግደል ወይም በመማረክ መሆኑን ስለሚያውቅ የወሰን ሰገድን ፕላን ለማፍረስ ብቻ ሳይሆን ንጉሡን የማባረሩ ጉዳይ ዓይነተኛ ዓላማው እንደነበር የታወቀ ነው ።

፪ኛ. በንጉሡም በራስ ወሰን ሰገድም አሳብ ለንጉሡ መሸሻ ዳሞት መመረጡን ዓይተናል ። ይህ ዳሞት የሚባለው አውራጃ ከጐጃም በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ ትልቅ አውራጃ ነው ። አሁን በመጨረሻ ስሙ በጐጃም ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ይመደብ እንጂ ቀድሞ ራሱን የቻለ ታላቅ አውራጃ ነበር ። በራስ ወሰን ሰገድ ውስጥ ሆነው ሊዋጉ የመጡትን የጋፋትን ፤ የጉራጌን ፤ የእናርያን ፤ የጅማን ሕዝብ ዓረብ ፋቂህ ስለጠቀሰ ከዚሁ ከታችኛው ዳሞት በስተ ደቡብ ያለው የዛሬ የወለጋ የጐሬ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ሁሉ ጋፋትና ጉራጌ ጭምር በዳሞት ነጋሽ ውስጥ ተጠቅለው የሚገዙ ይመስላል ። የግዛቱም ስፋት እስከ ዛሬው ወሊሶና እስከ አምቦ የሚደርስ ሳይሆን አይቀርም ።

፫ኛ ንጉሡ ከነጦራቸው ወደ ዳሞት እንዲሄዱ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት የዳሞት አገር ተራራማ ሥፍራና ጫካ ስለሞላበት ወደ ተራራው ሥፍራ የሚወስደውም መንገድ ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ አስቀድሞ ሥፍራውን ለያዘ ለመከላከል ይመቻል ፤ ለእንግዳ ጠላት ግን አስቸጋሪ ነው በማለት መሆኑ ጥርጥር የለውም ። የጫካነቱንም ብዛት ራሱ ስሙ የዝሆን ዱር መባሉ ይገልጻል ። በዛሬ አጠራር ይህ ሥፍራ የጅባት ጫካ ይመስላል ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 234 - 246

ዳሩ ግን ግራኝ አህመድና የጦር ሹማምንቱ ለዳሞትም ለማናቸውም አውራጃ
በፍጹም እንግዳ አልሆኑም ። ወደ ዳሞትም ወደሌላውም ወረዳ እፈለጋች
ሁት አውራጃ እስከ አክሱም ድረስ ልመራችሁ እችላለሁ ያለውን ያንድ በቅ
ርብ የሰለመ ክርስቲያን ንግግር እንደገና እናስታውስ ። አሸናፊውን ግራ
ኝን ለመምራት እርሱ ብቻም አይደለ ከሽምብራ ኩሬ ከአይፈርስና ከዛሬ
ጦርነት ወዲህ ከልብ ክርስቲያን ከነበረው ውስጥ ብዙው ተስፋ በመቁረጥ
ወደ ግራኝ መግባት ግዴታ ሲሆንበት ክርስቲያንነታቸው ወይም እስላምነታ
ቸው የለየውም ያልለየውም የደዋሮ ፣ የባሌ ፣ የይፋት ፣ የሐድያ ፣ የወጅ ፣ የጋ
ቱር ባላባቶች ውስጥ አንዳንዶቹ ባለፈው የክርስቲያን ሹማምንቶች አስተዳ
ደር እንደመጨቆን ቆጥረው በእስላሞቹ መንሣትና ማየል ደስታ እየተሰማ
ቸው በግራኝና በሹማምንቱ ዙሪያ ሆነው ባሸናፊውና ባዲስ ገዥ ፊት ሞገ
ስና ሹመት ለማግኘት በክርስቲያናዊው ሠራዊት ላይ ወሬ እንደነገሩ መን
ገድ እንደመሩ ፣ ስንቅ እንዳቀበሉ ናቸው ። ሁሉም ባሁኑ ሰዓት ደህና ምክር
ለማቅረብ አቋራጭ መንገድ ለመምራትና በግራኝ ለመመስገን አገልግሎታ
ቸውን ለማበላለጥ ይሻማሉ ። ምን ጊዜም ቢሆን በዚህ ዓለም ጊዜ ሰጥቶት
በሥልጣን ላይ ለተቀመጠ ሰው አገልጋዩ ፣ አማካሪው ፣ አስተናባሪው ብዙ
ነው ።

ከክርስቲያንነት ወደ እስላምነት የተለወጡው አዝማች ሃይቢ የተባለው
ISIC
የጋቱር ገዥ (አንዳንድ ጊዜ ዓረብ ፋቂህ ሃያቢል የሚለው) ንጉሡ ከዳሞት
ወደ ወጅ (ጉራጌና አሩሲ መካከል) ሸሽተው የመጡ ጊዜ ግራኝ ከሹማምንቱ
ጋር ሆኖ ምን ማድረግ እንደሚገባ ሲመካከሩና የቀሩት ሹማምንት ብዙ የን
ጉሡ ሀብት ወደ ተቀመጠበት ወደሸዋ እንሂድ ሲሉ ሃይቢ የለም ንጉሡ ወደ
ወጅ ከገባ መውጫ የለውምና ለኛ መልካም ሆነልን ከወጅ ወደ ጉራጌ አገር
ቢሸሽ የዚያ አገር ሕዝብ አይወደውምና አይቀበለውም ወደ ደዋሮ ቢሄድም
እንከታተለዋን እያለ ውትወታ ስላበዛ ግራኝ አንተ ዝም በል የነዚህ ምክር
ነው የሚሻለው ብሎ አሳፍሮት ወደ ሸዋ መጓዛቸውን ወደፊት እናነባለን ።
እነዚህንም ከመሳሰሉት ጋር ከሽምብራ ኩሬ ፣ ከአይፈርስ ጦርነት
ከሞት የተረፉት ግራኝ ለመሣሪያነት የሚፈልጋቸው ነገር ግን ገና እምነቱን
ያልጣለባቸው የክርስቲያን ሹማምንት እንደታሠሩ በዘበኛ እየተጠበቁ በግ
ድም በውድም ሲጠየቁ የሚያውቁትን መናገር ግዴታቸው ነው ፤ የሚያው
ቁትን አናውቅም ቢሉ እንደ ሃይቢ ያለው ወገኑን ከሐዲና ከሳሽ አይገድም ።
ስለዚህ በዚህ ጊዜ ኃይለኛውና ጨካኙ ግራኝ አህመድ የራሱ የፕላን እቅድ
ወይም የስንቅ ጉዳይ ካልገታው በቀር ንጉሡ ከደረሱበት ለመድረስ በፍጹም
የሚያስቸግረው ነገር ስለሌለ ማንም የውጭ ጠላት ተላልፎ ሊገባበት አይች
ልም የተባለውን በዳሞት የዝሆን ዱርን ጦርነት የሸሁን አጥር የቆዳ ጋሻ እያ
ስነጠፈ ቋጥኙን ደንጊያ እያስፈለጠ ጫካውን በሰይፍና በመጥረቢያ እያስመ
ነጠረ ንጉሡ ወደአሉበት በድንገት ተጠግቶ ተዋግቶ ለማሸነፍ ቻለ ።

፬ኛ. በዚህ በዝሆን ዱር ጦርነት ከሞቱት ውስጥ ዓፄ ልብነ ድንግል ዓምደ ሚካ ኤል ሞተን ? ብለው ሙኸው ያዘኑለት አባቱ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት የሞ ተው የዝግናው የሮቤል ልጅ መሆኑን እርሱም ያባቱን ሹመትና ደረጃ ይዞ በዝግንነት ከአቡበክር ጋር ሲዋጋ ከአቡበከር የተወረወረው ጦር በልቡ ገብቶ በዠርባው ከወጣ በኋላ የቁስሉን ጽናት ችሎ ከጠላቱ ከአቡበከር ጋር ድብደባውን መቀጠሉን የዓረቡ ጸሐፊ ሳይደብቅ ስለገለጠልን ዓምደ ሚካ ኤል በርግጥ የዝግና ልጅ ዝግና መሆኑን እንመለከታለን ። ከርሱም ጋር በመዠመሪያው ገሥግሦ መጥቶ ሺክ ሚካኤል የሚባለውን በጦር ወግቶ ከሞት ያደረሰውና ጦርነቱን የከፈተው ተክሉ (አንዳንድ ጊዜ ዓረብ ፋቂህ ተክላይ የሚለው) እዚህ ላይ በድጋሚ ሊታወስ ይገባል ። ተክላይ የሥራዬ ሹም መሆኑን በሌላ ቦታ ይገልጻል ። እነዚህም ሁሉ በዳሞት ከተማ የመን ገድ ወይም የተማረ ቤት ስያሜ ሊያገኙ የሚገባቸው መሆናቸውን በዚሁ እግረ መንገዳችንን እናስታውሳለን ።

፭ኛ. ዓረብ ፋቂህ ከዝሆን ዱር ጦርነት መልስ ላይ ታላቅ ዝናምና ብርድ ተነ ሥቶ በኡኢህ ያህር ቀድመው ከሚጓዙት የክርስቲያን ወታደሮች ውስጥ ፫፻ ሰው መሞቱን ግራኝ ስለሰማ ወደዚያ መሄዱን አቁሞ ወደ ገበርጌ ሄደ ይልና ከዚያ ወደ በረራህ (በረህ) በሠፈሩ ጊዜ ታላቅ ውሽንፍር ያለበት ዝናም ተነሥቶ ሰ[illegible]ጨልሞ ከነፋሱ ኃይለኛነት የተነሣ ድንኳኖቹ ምንቅር ቅራቸው ወጥቶ አንዳንዱ ድንኳን በአየር ላይ ያንዣብብ እንደነበር ግራኝ አህመድና ሚስቱ ሐጂራህ (የተከለ ሃይማኖት ሚስት የነበረችው) እንግዲህ ማለቃችን ነው ብለው ድንኳናቸውን አንቀው ይዘው በጭንቅ ወደ እግዚአ ብሔር ይጮሁ እንደነበረ ይገልጽና በኋላ ነፋሱና ዝናሙ ቆሞ ይኸስ ማየ አይህ ነው እያሉ መወያየታቸውን ያስረዳል (1) ።

ስለዚህ ከዳሞት (ዝሆን ዱር) በጉድሩና በግንደበረት አድርገው እንደገብ ጣን ወዳለበት ወደዛሬው የአዲስ ዓለምና የበቾ ግዛት ሲያመሩ ባንድ በከፍ ተኛ ቦታ ሠፍረው ሳለ ዋናው ክረምት ከመግባቱ በፊት ያለው የሚያዝያና የግንቦት ወይም የሰኔ ተግብ ተነስቶ አስቸግሯቸዋል ማለት ነው ። ነገር ግን ዝናሙ ከቆመላቸው በኋላ ግራኝ አብድ ኢን ናስርን ወደ እንደገብጣን ኡማር ሑሴንን ደራድባኒ ወደሚባል ወረዳ ለዘረፋ መላኩን እነዚህም ሁለት አለቆች በየበኩላቸው ሂደው አገር ሲዘርፉ አንዳንድ ጊዜ ለኔ በተመደበው ወረዳ ለምን መጣህ እየተባባሉ መጣላታቸውን ይገልጻል ። በዚህ ወረዳና በእ ንደገብጣን ከተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዱ በሰማዕቱ በቅ ዱስ ፊቅጦር ስም ንጉሡ ነገሥቱ አሠርተው በዚህ ሰማዕት ስም ለተሠየመው ለልጃቸው ለፊቅጦር የሰጡት ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ዓረብ ፋቂህ ያረጋ ግጣል ። ባዔ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፷ - ፲፬፻፸ ዓ. ም.) የዚህ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 246

የእንደገብጣን መምህር አቡቂር ይባሉ እንደነበረ ዜና መዋዕሉ ያመለክ ታል (1) ።

፯ኛ. ከዝሆን ዱር ጦርነት በኋላ የዓረቡ ጸሐፊ ከብርዱና ከነፋሱ ፤ ከመንገዱ ጭቃ ነት የተነሣ የእስላሞቹ ወታደሮች የነበራቸውን መድፍና ከክርስቲያኖቹ የማረኩትን አሥር መድፍ በድምሩ ፲፯ መድፎች በመንገድ እንደጣሉት ስለ ጻፈ ባዬ ልብነ ድንግል ሠራዊትም እጅ የመድፍ መሣሪያ መኖሩን ለመዝ መሪያ ጊዜ ይገልጽልናል ። እንዲያውም ቍጥሩን የእስላሞቹን ፯ ሲያደርግ የክርስቲያኖቹን ፲ አድርጎታል ። ይሁን እንጂ በነዚህ መድፎች ክርስቲያ ኖቹ አንድም ጊዜ እስላሞቹን በተራራቸው ላይ ሆነው አጠቁበት ማለት ቀርቶ አንድ ጥይት መተኮሱን በዚህም በሌላም ቦታ አመልክቶ አያውቅም ።

ምናልባት ይህ መድፍ በጥድፊያ በምጥዋ በኩል የትግሬዎቹ ሹማም ንት እንደምንም ብለው በቶሎ ገዝተው ንጉሣቸውን ለመርዳት ሲመጡ ይዘ ውት የመጡትና ነገር ግን የመሣሪያውን አሠራርና አተኳኰስ የሚያውቅ ደ.ህና መድፈኛ የላቸውም ይሆናል ። ወይም ቀድሞ የነበረ አሮጌ ምንም የማይ ሠራ እንደሆነ አይታወቅም ።

፰ኛ. ራስ ወሰን ሰገድ ከዳሞት መጥቶ ተስፋ ለመቁረጥ በቀረቡት ሹማምንትና መኳንንት መካከል ተገኝቶ በአዲስ ጉልበት ግራኝን የመቋቋም መንፈስ መፍ ጠሩ ፤ በሕይወት ላሉት አለቆች ዋና ተስ[illegible]ሆኑ ፤ የንጉሡን ሕይወት ለመ ከባከብ ወደ ዳሞት ንጉሡን ልኮ እርሱ የግራኝ ወገኖች ወደሚገኙበት ወደ ደ.ዋሮ ወደ ሐረር አመራለሁ ማለቱ ሲያስመሰግነው ግራኝ የርሱን አሳብ በቅ ድሚያ አውቆ ወደ ንጉሡ እንጂ ወደርሱ አለመኄዙን ሲያውቅ በምን ምክን ያት ወደ ግራኝ ተመልሶ በዚያ በጠባብ መንገድ ከንጉሡ የጦር ሹማምንት ከነዓምደ ሚካኤል ጋር በፈረስ ጋላቢና በሯጭ በኩል ተላልኮ ግራኝን በፊ ትና በኋላው እንዲወጋ አላደረገም ።

ይህ ዕድሜው የገፋ ታላቅ የጦር አለቃ ባንድ ወገን ንጉሡ ነገሥቱ ሹማምን ቱና ሕዝቡ በርሱ ላይ የጣሉት እምነት የአገሩንና የሃይማኖቱን ጠላት ግራኝን ለመ ውጋት ከልብ ሲገፋፋው በሌላው ወገን የገፋው ዕድሜው ከግራኝ ጨካኝነትና ተዋ ጊነት ጋር ተባብሮ መንፈሱን ሰቅጠጥ በማድረግ ጊዜ እንዲያራዝም ያስገደደው ይመስላል ። ብዙ ዕድሜ በፊቴ አለኝ ከሚል ወጣት ለመሞት የቀረኝ ዕድሜዬ ጥቂት ነው የሚል ሽማግሌ ለሕይወቱ እንደሚሳሳ የታወቀ ነው ።

(1) ገጽ 107 - 133 - 134

## ምዕራፍ ፶፭

## የደብረ ሊባኖስ ገዳም መቃጠል - የመነኮሳቱ ከነበልባሉ ውስጥ መግባት
## (፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ሐምሌ ፳፱ ቀን)

ታሪክ ነገሥቱ ከአይፈርስ ጦርነት በኋላ በዛሬ የተደረገውን ጦርነት ራስ ወሰን ሰገ ድና ግራኝ አህመድ የተላላኩትን የዛቻ መልእክት በዝሆን ዱር ላይ የተደረገውን ውጊያ ሁሉ ዘሎ ከአይፈርስ ጦርነት በቀጥታ ወደ ደብረ ሊባኖስ ቃጠሎ ተሻግሮ ባጭሩ ከዚህ በፊት እንዳነበብነው እንዲህ ሲል ይናገራል . . . . . ። «ግራኝ በአይፈ ርስ ተዋጋ - በሚያዝያ ፳ ቀን ራስ እስላም ሰገድና ተክለ ኢየሱስ ሌሎችም መኳን ንት ሞቱ ፤ ሸዋንም ገዛት ። ከዚያ በሐምሌ ፳፱ ቀን ደብረ ሊባኖስን አቃጠለ ፣ በነ ሐሴ ፳ ቀን ራስ ወሰን ሰገድ ሞተ» (1) ።

የደብረ ሊባኖስን ቃጠሎ ከዓረብኛ አቈጣጠር ጋር በማስተያየት ሙሴ ሬኔ ባሴት እ.ኤ.ዮ.ሐምሌ ፲፯ (በኛ ሐምሌ ፱ ቀን) አድርገውታል ። ነገር ግን በዚህ ረገድ የታሪክ ነገሥቱን ቀን መሠረት ማድረግ የሚሻል ይመስለኛል ። እርሱም ከላይ እንደተመለከትነው ቃጠሎውን ሐምሌ ፳፱ ቀን የተክለ ሃይማኖት በዓል በዋ ለበት ቀን አድርጎታል ። ምናልባትም በዕለተ ቀናቸው ኢቃጠላቸው ለማስኘትና አማኙን ተስፋ ለማስቆረጥ ታስቦ የተደረገ ይሆን ? ።

የደብረ ሊባኖስ ገዳም ታሪኩን ቢቀር ስሙ ጥሩነቱን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ አይገኝም ። ትክሉ በ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. መጨረሻ ወይም በ፲፬ኛው መቶ ዓ. ም. መዠመሪያ ላይ ሳይሆን አይቀርም ። ከዚያ ወዲህ የተነሡ የቤተ ክህነት አባቶች የተክለ ሃይማኖትን አጽም ከአሳረፉበት ወዲህ ገዳሙ ይበልጥ እየገነነ ሄደ ። ከዚህ ቀደም ባዔ ይኵኖ አምላክና ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ላይ እንዳመለከት ነው የቀድሞ ስሙ ደብረ አስቦ ነበር ። በኋላ ግን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመናቸው ደብረ ሊባኖስ የሚል አዲስ ስያሜ አወጡለት ። ይህም ገዳም የአቡነ ተክለ ሃይማ ኖት ዓጽም ካረፈበት ወዲህ በነገሥታቱም በሕዝቡም ዘንድ እየከበረ ሄደ ። በገ ዳሙ አጠገብ ድውይ ይፈውሳል የሚባለውን ጠበል ለመነከር ፣ ገዳሙን ለመሳ ለም ከየአውራጃው የሚሰበሰበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ነው ። ሕዝቡና መኳንን ቱም በዚህ ገዳም ለበዓል አብዛኛው ጊዜ የሚሰበሰቡት ባመት ፫ ጊዜ ነው ።

፩ኛው ታኅሣሥ ፳፬ ቀን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱበት ፣

፪ኛው ግንቦት ፲፪ ቀን አጽማቸው የፈለሰበት (ከደብረ አስቦ ገዳም ወደ ታላቁ ሕንፃ ወደ ደብረ ሊባኖስ የተዛወረበት)

፫ኛው ነሐሴ ፳፬ ቀን ያረፉበት ነው ።

እስከ አሁን ድረስ እንደሚደረገው በነዚህ ቀኖች በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚ

(1) ወገብረ ፀብዓ በአይፈርስ እመ ፳ ለሚያዝያ ወሞቱ ራስ እስላም ሰገድ ወተክለ ኢየሱስ ወብዙ ኃን መኳንንት ወመለከ ለሸዋ ። ወእመ ጽ፱ ለሐምሌ አውዓያ ለደብረ ሊባኖስ ። ወእመ ፳ ለነ ሐሴ ሞተ ራስ ወሰን ሰገድ ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 92 ። ባሴት ሬኔ ያሳተመው ገጽ 328 ።

ደረገው ክብረ በዓል ታላቅ ነው ። ጠበሉን የሚጠመቀው ሥለት የሚያገባው እዚያ ብቀበር እጸድቃለሁ ብሎ ተስፋ የሚያደርገው ብዙ ነው ። ስለዚህ ይህ ገዳም የመንግሥቱ መደብ ሸዋ በነበረበት ወደ ጐንደርም በዞረበት ጊዜ በመላው ኢትዮ ጵያ በተለይ በሸዋ የተከበረ ገዳም ነበርና አሁን ግራኝ የንጉሡን ጦር አሸንፎ ፈጠ ጋርን ደዋሮን ባሌን ይልቁንም ሸዋን ከወረረ በየአውራጃው በፈጠጋር ያንጊዜ ባደቄ (ዛሬ ዱከምና ቢሾፍቱ) እንዶጥናህ (ዛሬ አዲስ አበባ) አካባቢው ሁሉ እየተ ዘረፈ ከተቃጠለ በኋላ ንጉሡና ራስ ወሰን ሰገድ ከዝሆን ዱር (ጅባት) ታች ታቹን በዛሬው ሶዶ ቡታ ጅራ ዝቋላ አድርገው ወደሸዋ በሚጓዙበት ጊዜ ያንድ ክፍል ጦር እንደያዘ በብዙ የጦርነት ቦታ የዋለው ቀጭኑ አቡበከር ያን ጊዜ ግራርያ በኋላ ሰላሌ ወደተባለው ወረዳ አመራ ።

አቡበከር ወደዚህ ወረዳ ደርሶ የማሳመን ሥራውን በሚያከናውንበት ሰዓት ሀብቱን በሙሉ ወስዶ ከመነኰሳቱና ከዙሪያው ሕዝብ ግብር ተቀብሎ በመነኰ ሳቱ ልመና ገዳሙን ከቃጠሎ ለማዳን ከጅሎ ነበር ። ዳሩ ግን ከዚህ በፊት እንዳመ ለከትነው ከበለው ዘር ተቆርጦ ወደ ሱማሌ አገር ከወረደው በለው አብደላ ከሚ ባለው ወገን የሆነ አንድ ሰው ከአለቃው ተደብቆ ገዳሙን እሳት ለኩሶ አቃጠለው። ገዳማቸውን አጥብቀው የሚያፈቅሩ መነኰሳት በፈቃዳቸው እሳቱ ውስጥ እየገቡ አብረው ተቃጥለው በሰማዕትነት አረፉ ።

ዝርዝር ታሪኩን ከዚሁ ከዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ላይ እነሆ እንመልከት ። «እስላ ሞቹ በበራራህ ፯ ቀን በሰነበቱበት ጊዜ ያገሩ ሰዎች አጠገብህ ታላቅ ቤተ ክርስቲ ያን (ገዳም) አለች ብሎ ለይማም ነገሩት እርሱም ወዴት አገር ቢል ግራርያ በሚ ባል አገር አውርማህ በሚባል ወንዝ ዳር ነው ። ስሙም ደብረ ሊባኖስ ይባላል። ክርስቲያኖቹ ሁሉ ወደዚያ እየሄዱ ተሰብስበው ያከብሩታል ። በያይነቱ ልብስ የወ ርቅና የብር ጥዋ እንደ ዛፍ ግንድ የወፈረ ጧፍ ይሰጡታል ። በአበሻ አገር ከተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት እርሱ አንደኛ ነው ። ከአክሱምና ከላሊበላው ቤተ ክርስቲ ያን በቀር የሚተካከለው የለም ብለው መለሱለት ከዚህ ስንት ቀን ያስሄዳል ብሎ ቢጠይቃቸው ፯ ቀን ያስሄዳል አሉት ።

ስለዚህ ኤሚር አቡበከር ቀጢንን አስጠርቶ እንኤሚር ሙጋሂድ ፤ እንአብሳማ ኑር ፤ እንነድል ሰገድ ያሉበትን ፫፻ የፈረሰኛ ጦር ሰጥቶ እንዲዘምት ላከው ። እርሱም ከነጦሩ ወደዚያው (ወደ ደብረ ሊባኖስ) ሄዶ በአቅራቢያው ሠፈረ ። ይኸን ሲሰሙ መነኰሳቱ ሰው ወደማይደርስበት ተራራ ሸሽተው ሄዱ ። በኋላ ግን ግማሾቹ ገዳማ ችን ሲቃጠል ከመሸሽ አብረን ብንቃጠል ይሻላል ብለው ተመልሰው ወደ ገዳማ ቸው መጡና እሳቱ እስኪለኮስ ድረስ እገዳሙ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ ። የቀ ሩት መነኰሳት ይኸን ገዳም በማቃጠል የምትጠቀሙበት ነገር የለም ይልቅስ እኛም እንደምትፈልጉት ያሀል ወርቁን ፤ ብሩን ፤ ልብሱን እናስረክብ በገዳሙ ዙሪያ የሚገኘውም ሕዝብ ግብር ያግባና ገዳሙን ከቃጠሎ አድንልን ብለው ወደ ኤሚር አቡበከር ቀጢን (ቀጭኑ አቡበከር) ላኩ ።

ከዚህ በኋላ አቡበከር ከጓደኞቹ ጋር ስለዚህ ጉዳይ ምክር ያዘ ። ግማሹ ሀብ

ቱን ወስደን ገዳሙን እንተው ፤ የቀሩት ደግሞ ይህ ገዳም በክርስቲያኖቹ ዘንድ በጣም የከበረ ስለሆነ ገዳሙ ይቃጠልና ገንዘቡ ይቅርብን አሉ ። አቡበከር ግን ሀብ ቱን ወስደን ገዳሙን እናቃጥል ያሉትን ሰዎች አሳብ ደግፎ መላክተኛውን ጠራና መልካም ነው ሀብቱን ካስረከባችሁ ገዳሙን ትተናል ። ስለዚህ ጓደኞችህ ይምጡና የምንፈልገውን ሀብት እናስታውቃችኋለን ከሰጡንም በኋላ ገዳሙን ከማቃጠል እንተዋለን ብሎ ነገረው ። መላክተኛው ተመልሶ ሄዶ ለጓደኞቹ በነገራቸው ጊዜ ደስ አላቸው ወደ አቡበከርም መጥተው ተገናኙና ይኸን የደስታ ወሬ ስለአሰማቸው በላዩ ላይ ፱፻ ወቄት ወርቅ ክብ ጌጥ (ጥላክ) ያለበት ሁለት ልብስ እንደዚሁም ፱፻ ወቄት ንጹሕ ወርቅና ብርም አቀረቡለትና ይህ ያሁኑ ስጦታችን አላቃጥልም ብለህ ለነገርኸን የደስታ መግለጫ የሚሆን ብቻ ነው ። ነገር ግን ሕዝቡ በሰላም ወርቅም ብርም ሊገብርህ የሚገባውን ቁረጥና ንገረን ብለውት የዚህኑ ጉዳይ ከአቡ በከር ጋር ሲነጋገሩ አንድ አውራይ አቡበከር የሚባል ነገዱ በለው (ማሐዊራሀ) የሆነ ከአገሩ ከትግሬ ወደ ሰዓድ ዲን አገር (አዳል) ወርዶ ልጁን ያገባው የበለው አብደላ ዘር የሆነ . . . . . . በድብቅ የችቦ እሳት ይዞ ሄዶ ገዳሙን ለኩሶ አቃጠለው ። በዚህ ጊዜ መነኰሳቱ ከአቡበከር ቀጢን ጋር ሲነጋገሩ ዘወር ቢሉ ቃጠሎውን አዩ ። ነበልባሉም እስከ ሰማይ ወጥቶ ነበር ። መነኰሳቱ ይኸን ሲያዩ የሰላም ድርድራቸውን አቋርጠው እሳቱ ላይ ለመውደቅ እምሯቸው እየሮጡ ሄደው ጥቂቶቹ ብቻ ሲቀሩ የቀሩት ሁሉም እንደ እሳት እራት እነበልባሉ ውስጥ ተወረወሩ ።

ኤሚር አቡበከር ቀጢን አውራይ አቡበከርን አስጠርቶ አስመጣውና እኔ የሰላም ነገር ስደራደር በምን ምክንያት አቃጠልህ ብሎ ጠየቀው ። እርሱም እኔ ነኝ ያቃጠልሁት የፈቀድኸውን አድርገኝ ይማም እንድናቃጥል እንጂ በገንዘብ የሰላም ውሉታ እንድናደርግ አልላከንም ብሎ መለሰለት ። ኤሚር አቡበከርም እርሱንና የተገኘውን ምርኮ ይዞ ወደ ይማም ዘንድ ተመለሰ ። ፲፪ ቀን ያህል እንደተጓዙ እይማም ዘንድ ደረሱና ኤሚር አቡበከር አውራይ ገዳሙን ማቃጠሉን ነገረው ። እርሱም ደግ አደረገ እኔም የላክኋችሁ እንድታቃጥሉ ነው ፤ ለእናንተም ከዚህ (ከማቃጠል) የሚበልጥ ቁም ነገር ያለው ነገር የለም ። አሁንም ሄደህ እሠፈርህ እደርና የምነግርህ ጉዳይ አለኝና ነገ ተመለስ'' አለው» ሲል ዓረብ ፋቂህ ይተርካል (1) ።

ወደ ደብረ ሊባኖስ ሊዘምት የመጣው ይህ አቡበከር ቀጢን ባለፈው ምዕራፍ እንደተጻፈው በዚሁ በግራኝ ጦርነት ጊዜ በብዙ ቦታ ላይ ራሱ አዝማች እየሆነ ለብቻው ብዙም ጊዜ በግራኝ ውስጥ ሆኖ በብዙ የጦር ግንባር ተዋግቷል ። ታሪነ ነገሥቱ እንደሚተርክልን ከአራት ዓመት በፊት በ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ራስ ደገልሃን አዳልን ወርሮ ብዙ ሕዝብ የማረከ ጊዜ የአቡበከር ቀጢን እናት ፋጥ የምትባለው አብራ ተማርካ ሳለ ከግራጥ ጋር በድንገት መጥተው በራስ ደገልሃን ላይ አደጋ ጥለው አሸንፈው አቡበከር እናቱን እንዴት እንዳስመለሰ ከተገጠመለት ግጥም ጋር አንብበናል ። ከዚያ ወዲህ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በሽምብራ ኩሬ ጦር

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 246 - 256

ነት አዝማች አሮንን ፣ በአይፈርስ ጦርነት ዘምቢልን በዝሆን ዱር (ዳሞት) ጦርነት ስመ ጥሩውን ዝግና ዓምደ ሚካኤልን (የሮቢልን ልጅ) የገደለ እርሱ ነው ። ከቃ ግማ ግራኝ አህመድ በጥብቅ የሚፈልገውን ተክለ ሃይማኖትን በጠቋሚና በደፈጣ ሄዶ አዘንግቶ ተዋግቶ ከነሕይወቱ ማርኮ ከሚስቱ ጋር ለግራኝ ያቀረበ እርሱ ነው። ወደፊትም ይኸንኑ የመሰለ አገልግሎቱን ሲቀጥል እንመለከታለን ።

ግዕዝኛው ታሪክ ስሙን ቀጭን አቦከር ይለዋል ። ዓረብኛውና ግዕዙ አማርኛውም ተስማምተው ቀጭኑ የሚሉት ሰውነቱ ረዥም ቀጭን ስለነበረ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ ወደ ደብረ ሊባኖስ ለዘመተው ጦር የበላይ አለቃ በሆነበት ጊዜ መነኰሳቱ የገዳሙን ሀብት ካስረከቡን በዙሪያው ያለው ሕዝብ የጠየቅነውን የሚገብር ከሆነ ገዳሙን ከማቃጠል መተዉ ይሻላል ብሎ ከመነኰሳቱ ጋር የሰላም ውል መደራደሩ ያስተዋይነት ሥራ ነበር ።

ዳሩ ግን አውራይ አቡበከር ተደብቆ ስለአቃጠለው ምንም ማድረግ አልቻለም ። ሊቀጣውም ፈልጎ ግራኝን በመፍራት የተወዉ ይመስላል ። በግራኝ መንፈስ ውስጥ ያለውን የክርስትና ምልክት የሆነውን የመደምሰስና የማጥፋት ዓላማ ከዚያኛው ይበልጥ ቀጭኑ አቡበከር ያውቃል ። አውራይ አቡበከር አለቃው አቡበከር ቀጢን ለእርቅ በሚደራደርበት ጊዜ ደፍሮ ማቃጠሉ በዋናው ጠቅላይ መሪ በግራኝ ፈቃድና መንፈስ ውስጥ ያለውን በመተማመን ነው ።

አቡበከር ገዳሙን ለመተው ሲፈልግ ያኛው ለማቃጠል የቻኰለበት ምክንያት ከትግሬ ወደ አዳል ተዛውሮ የባላባቱን ልጅ አግብቶ የተቀመጠው የበለው ዘር ከፍ ያለ ቂምና ጥላቻ ከትግሬ ካማራ ክርስቲያኖች ጋር ስለነበረውና የቂሙ ሐረግ እስከዚሀ እስከ አውራይ አቡበከር ደርሶ ያንኑ ቂም ለመወጣት ያደረገው ይመስላል ። የቦኃስ የአገው (የበጅያ) የቢለን ዘር ከሴማዊው ዘር ከነገደ ዮቅጣን ከወረደው ከአማራና ይልቁንም ከትግሬ ዘር ከቀድሞ ከአክሱም መንግሥት ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በቋንቋ ፣ በልማድ ፣ በሃይማኖት የተለያዩ ስለሆኑ የዘወትር ግጭታቸውና ጦርነታቸው የበረታ ነው ። በዛኊዬ ጊዜ እረፍት ያገኙ ቢመስልም ከዚያ ወዲህ በክርስቲያኖቹ መጠቃታቸው የቀረ አይመስልም ። ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በለው አብድ አላ የዚህ ያቃጣዩ ዘር በ፲፫ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ላይ ከትግሬ ወደ አዳል ከነቤተ ሰቡ ዞሮ መቀመጡ ጥቃትና ጠብ ሰልችቶት ይሆናል (1) ።

ISIC

አሁን የዚህን ጉዳይ አልፈን ከገዳሙ ጋር አብረው ወደተቃጠሉት መነኰሳት ጉዳይ እንተላለፍ ።

የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ባለፈው እንዳነበብነው ከዝርዝር ታሪክ ጋር የመነኰሳቱን ተቃጥለው በሰማዕትነት መሞታቸውን ሲነግረን የራሳችን ታሪክ ነገሥት ወአመቷወ፩ ለሐምሌ (ግራኝ) አውዓያ ለደብረ ሊባኖስ ብሎ ከማለፍ በቀር የመነኰሳቱን አስደናቂ ሰማዕትነት አያነሣውም ። ባዬ ሠርዬ ድንግል ወይም ባዬ ሱስንዮ

(1) የሬኔ ባሴት ማስታወሻ ቍጥር 1 በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ገጽ 255

ዮስ ዘመን የተጻፈ የሚመስል አጭር ያዔ ልብነ ድንግል ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒ ወደ ኢጣልያን ተርጉሞ ከግዕዙ ጋር ያሳተመው «ይቺ ዓመት (፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) ከማ ለፉ በፊት በሐምሌ ፳፬ ቀን እንዲቷን የሐዋርያት መሰብሰቢያ የሆነችውን የተ ክለ ሃይማኖት መቃብር ያለባትን ደብረ ሊባኖስን አቃጠላት» ብሎ ወደ ሌላ ጉዳይ ስለሚያልፍ ከፊተኛው የተሻለ ዝርዝር ሊሰጠን አልቻለም (1) ።

ስለዚህ ለሃይማኖታቸውና ለገዳማቸው ጥብቅ ፍቅርና ቅናት ያላቸው እነዚህ መነኰሳት የዚህን ዓለም ኑሮ ንቀው ማንም ሳያስገድዳቸው በፈቃዳቸው እሚቃጠለው ነበልባል ውስጥ ገብተው ሲሞቱ ስማቸውን ከነዝናቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ ለመዘርዘር ባለመቻሉ አዝናለሁ ። እንዲያውም ይኸን የመሰለ ተጋድሎ የፈጸሙ መነኰሳት አሁን በሚገኘው በደብረ ሊባኖስ ገዳም እዋናው መግቢያ በራፍ ላይ ለያንዳንዳቸው እንኳ ባይቻል በሁሉም ስም አንድ ትልቅ ነዋሪ ሐውልት ሊሠራላቸው ይገባል ። ስማቸው በገዳሙ ጽሑፍ ውስጥ ምናልባት ቢገኝ ሊዘረዘር ቢጠፋ ባጭሩ "ግራኝ አህመድ ኢትዮጵያን የወረረ ጊዜ በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ሐምሌ ፳፬ ቀን የደብረ ሊባኖስ ገዳም ሲቃጠል በፈቃዳቸው አብረው የተቃጠሉ መነኰሳት መታሰቢያ" ተብሎ ሊቀረጽላቸው ይገባል ።

በገዛ ፈቃድ መሞት መጽሐፍ ስለሚከለክል ያስኰንናል ለሃይማኖታቸው ነውና ያደረጉት ያጸድቃል የሚል አከራካሪ ጉዳይ ቢኖርበትም አሟሟታቸው ካገርና ከወገን ፍቅር ጋር በተ[illegible] ሁኔታ ስለሃይማኖታቸውና ስለሚወዱትም ገዳም ነውና ራሳቸውን የሠዉት በፈቃዳቸው በመሞታቸው ቢጸድቁም ቢኰነኑም በዚህ ገዳምና ታሪክ ውስጥ ስማቸውና ዝናቸው ሊታወስ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፶፪

## ግራኝ ንጉሡን ከማባረር ሀብት ማባረርን እንደመረጠ — የራስ ወሰን ሰገድ ጦርነትና ሞት ። (ነሐሴ ፳ ቀን ፲፭፻፳፫ ዓ. ም.)

ራስ ወሰን ሰገድ የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍና ከዚህ በፊት ያነበብነው ታሪክ ነገሥት እንዳመለከተን በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ከነበሩት ታላላቅ ሰዎች የበለጠ ትልቅ ሰው ነው ። ትልቅነቱን ከሚያስረዱት ዋነኞች ምክንያቶች ገና ባዔ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ከዳተኛው ወንድሙ ወናግ ዣን በከዳተኝነቱ ሊታሰር ወይም ሊገደል ይገባው የነበረውን በአማላጅነቱ አስምሮ ማሾሙ (2)፣ ባሁኑ በግራኝ ወረራ ጊዜ ከአይፈርስ ውድቀት በኋላ በንጉሡ ጥሪ ከዳሞት የመጣ ጊዜ በአያቶቻችሁና በአባቶቻችሁ ጊዜ አድርገውት የማያውቁትን እነዚህ እስላሞች አሸነ

(1) ወእመ ቅድመ ኀልፈተ ይእቲ ዓመት (፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) አውዓያ ለደብረ ሊባኖስ መቃብረ ተክለ ሃይማኖት እሐቲ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት እመ ፳ወ፬ ለሐምሌ ገጽ 13 - 23

(2) ዓረብ ፋቂህ 164 - 165

ፏችሁ ። ይኽ ሁሉ መከራ የደረሰው በሕዝብ ላይ በፈጸማችሁት ግፍ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነው ብሎ ሹማምንቱን በንጉሡ ፊት ለመውቀስ መቻሉ ፣ ሹማምንቱ በወቀሳው በመቀየም ፈንታ እንግዲህ አንተ ከመጣህልን በፊትህ እየተዋጋን እንሞታለን ማለታቸው ሹማምንቱ በርሱ ላይ ከፍ ያለ እምነት እንዳላቸው ያስረዳል ። በኋላ ደግሞ ከዝሆን ዱር ውጊያ ወዲህ አዋሽ ዳር ሊዋጋ ሲዘጋጅ እዚህ ተዋግተህ ብትሞት የሃይማኖታችን ፍጻሜ ይሆናል ስለዚህ ወደቦሰት ተራራ ሄደን እዚያ መከላከሉ ይሻላል ሲሉ በዚህ ተስፋ በሚያስቆርጥ የጦርነት ሰዓት ለሁሉ አለኝታና ተስፋ ሆኖ የተገኘው ራስ ወሰን ሰገድ ስለሆነ ሁሉም ስለርሱ ሕይወት እየሳሳ ይከባከበዋል ማለት ነው ።

ይኽን የመሰለው እምነት በነአዛዥ ደገልሃንም በሌሎቹም ይልቁንም እንደርሱው የግራ ቢትወደድነት ማዕርግ ባለው በቢትወደድ ሠርፄ ላይ ሲጣል አልታየም ። በስሙ ከግራኝ አህመድ ጋር መጻጻፉ ራሱ አንድ ታላቅነቱን የሚመሰክር ነው ። ይህ ታላቅ ሰው በአይፈርስ ፣ በሽምብራ ኩሬ ፤ በዝሆን ዱር አባቶቻችሁ ተሸንፈው የማያውቁትን እንዴት አሸነፏችሁ እያለ በመገረም ሹማምንቱን የወቀሰበትን ውጊያ ራሱ ገጥሞ የጦርነቱን መራራ ሐሞት ራሱ ሊያጣጥም ነው ። ግራኝንም መጣሁ ጠብቀኝ ያለበት ጦርነትም በሚያሳዝን አኳኋን ለራሱ መሞቻ ሆነ ።

በዚህ በታላቅ ሰውዬ አለኝታ ምክንያት ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል በዝሆን ዱር በሩን ይዘው በመከላከል እነ ዓምደ ሚካኤል ከ[illegible]ወዲህ ወደሰሜን ወደ ቤተ አምሐራ በመሸሽ ፈንታ ግራኝ እርሳቸውን ሲያባርር አልፎበትና ዘርፎበት ወደ ነበረው ወደ ምሥራቅ ወደ ወጅ (ወንጂ) መጡ ። ከዚያም ወደ ገበርጌ መጥተው ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር ተገናኝተው ምክር ያዙ ።

ይህ ታላቅ ሰው እንደዚህ የተከበረ የተፈራ ሹማምንት እምነታቸውን የጣሉበት ሲሆን እስካሁን እንደምን ጦርነቱን ሳይካፈል እንደቆየ በትክክል ለማወቅ አይቻልም ። በአሁኑ ሰዓት ይነስ ይብዛ ታላላቆቹ ሰዎች ጦርነቱን እየተካፈሉ ግማሾቹ መሞታቸውን ባለፈው አንብበናል ። የገበዘ አክሱም መጽሐፍ ግራ ቢትወደድ ወሰን ሰገድ ፤ ቀኝ ቢትወደድ እስላም ሰገድ እያለ ከርሱ ጋር ብዙ ጊዜ የሚያቀናጃቸው ራስ እስላም ሰገድ ከትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ጋር ሆኖ በአይፈርስ ጦርነት ተዋግቶ በዛሪ ሞቷል ። በደዋሮ የተዋጋው ከአይፈርስ አዝማችነት በብልጠት የተዛወረው አዛዥ ደገልሃን በባደቁ የተዋጋው ቢትወደድ ሠርፄ በደዋሮ የተዋጋው ራስ ነቢያት እነዚህን የመሳሰሉ ከሽምብራ ኩሬ ከሌላውም ጦርነት እየተዋጋው ራስ ነቢያት እነዚህን የመሳሰሉ ከሽምብራ ኩሬ ከሌላውም ጦርነት እየተዋጋ ወደፊት ለመዋጋት በንጉሡ ዙሪያ ይገረፉ የንጉሠ ነገሥቱን ሕይወት እየጠበቁ ወደፊት ለመዋጋት በንጉሡ ዙሪያ ይገኛሉ ።

በአልቫሬዝ መጽሐፍ ላይ ስማቸው ተጠቅሶ የምናገኘው ባሕር ነጋሽ ዶሪ የንጉሡ አጎት (1) ራስ አደራው ፤ ራስ ተክሌ ፤ ራስ ያዕቆብ (2) ፤ ቄስ ዓፄ የነበረው

(1) አልቫሬዝ ዶሪንና አርገን የሉቴኔ ናየድ ሞገሳ ወንድሞች ያደርጋቸዋል ።
(2) አልቫሬዝ ምዕ. 24 ገጽ 53

ያዬ ልብነ ድንግልን እጎት የሚያገባው የተከበረው አቡሄር ፤ የዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ልጅ (1) የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ እብዲናን (2) ፤ እነዚህን ሁሉ ዓረብ ፋቂህ ስለማያነሣቸው ወይም በሹመት ስማቸው ብቻ ስለሚያነሣ በዚህ ጊዜ ምን እንደሚሠሩ አይታወቅም ፤ ግማሾቹ ሞተው ግማሾቹ በንጉሡ ዙሪያ ግማሾቹ በግዛታቸው ይገኙ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ጦርነቱ ከተዠመረ ፬ ዓመት አልፎት ሳለ ይህ ታላቅ ያገርና የጦር መሪ ራስ ወሰን ሰገድ ጦርነቱን ሳይካፈል እስካሁን እንደምን ቆየ የሚል ጥያቄ ይመጣብናል ። ለዚህ መልስ በራሱ አነጋገር ይህ መከራ የደረሰው ሕዝብን በመጨቆናችሁ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነው ስላለ ምናልባት ወደ መጨረሻ ጊዜ በመንግሥቱ አስተዳደር ቅያሜ ገብቶት በንጉሡ ትእዛዝና በራሱም ፈቃድ በዳሞት ግዛቶ ግማሽ ግዞተኛ ሆኖ ተቀምጦ ይሆናል ። በዚህም ላይ ሽምግልና ስለተጫነው ይሁን ደዋሮን ሲገዛ ሳለ ከግራኝ መምጣት ቀደም ብሎ የገዛ ልጁን ባሕር ሰገድን ለደዋሮ ግዛት ትቶ እርሱ ወደ ዳሞት ሄደ ሲል ዓረብ ፋቂህ ስለሚያረጋግጥ ለሹመት ልጁን ተክቶ እርሱ ወደ ዳሞት ወደ ጉልቱ ሄዶ ይሆናል (3) ። በእንደዚህ ያለ ጦርነትና የመከራ ሰዓት እንደዚህ ያሉ ሕዝብ የሚወዳቸው ታላላቅ ሰዎች በግድም በውድም መፈለጋቸው ስለማይቀር በዚሁ ዓይነት ወሰን ሰገድ በንጉሡ ባዬ ልብነ ድንግል ጥሪ ያን ሁሉ ሕዝብ ሰብስቦ መጥቶ እነሆ ከግራኝ አህመድ ጦር ጋር ተሰልፏል ። እንግዲህ ወደ ጦርነቱ እንመለስ ።

ግራኝ አህመድ ባለፈው ሁሉ እንደተገነዘብነው ወረራውንና ውጊያውን የሚፈጽመው የራሱ ነባር ሹማምንትና አዲስ የገቡለት አለቆች የሚያቀርቡለትን አሳብና መላ አዳምጦ የሚሻለውን ከመረጠ በኋላ ነው ። የርሱ አሳብ በየመስመሩ ከቀረበለት አሳብ የተሻለ መሆኑን ሲያምን በራሱ አሳብ ይመራል ። አንዳንድ ጊዜ የተሻለ በመሰለው በሌሎቹ ይመራል እንጂ አዛዡ ናዛዡ እኔ ነኝ በማለት የራሱን ፈቃድ ብቻ በማስፈጸም ሹማምንቱን ተጭኖ አያስቸግርም ። እርሱ በጥብቅ የሚከተለው ከግሉ ፈቃድና ከግል ጥቅሙ ከግል ሥልጣኑ ይልቅ የጠቅላላውን የአገዛዝ ዓላማ ብቻ ነው ። ይኸን የመሰለውም ነፃ አሳብ የመስጠትና የመቀበል ዕድል በዓለም የከፍተኛ መሪዎች ሀብትና ስጦታ ነው ። በዚህ ዓይነቱ አመራር ሁሉም በየበኩሉ ኃላፊነት ስለሚሰማውና ልባዊ ኅብረት ስለሚያሳይ ዞሮ ዞሮ ጥቅሙ የበላዩ መሪ ነው ።

በዚህ ምክንያት ንጉሡን ዓፄ ልብነ ድንግልን ማባረር ዓይነተኛ ዓላማው ሆኖ ሳለ ከዝሆን ዱር ሸሽተው ወደ ወጅ (ወንጂ) የገቡ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባ ምክር ሲደረግ ከዳተኛው አዝማች ሐይቤ ንጉሡ ወጅ ከገባ ለኛ ሆኑልን በግሥጋሴ ሄደን ልንይዘው እንችላለን ብሎ ሲመክርና ወገኖቹ እነገራድ አህሙሹ እነኤሚር ሑሴን ንጉሡን ለመከታተል ወደ ወጅ የሄድን እንደሆነ ወጅ ለደዋሮ ደዋሮም ለሐ

(1) አልፍራጽ ምዕ. 21 ገጽ 46
(2) አልፍራጽ ምዕ. 108 ገጽ 270
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 175

ረር ስለሚቀርብ ወደዚያ ስንሄድ አገሩ ለመመለስ የናፈቀው ወታደር እየከዳ ተበ
ታትኖ ወደ አገሩ ይገባል ። ስለዚህ ወጅን ትተን ክረምቱ እስኪወጣ ድረስ የቤተ
መንግሥት ሀብት ወደሞላበት ወደሸዋ ሄደን እንዝረፍ ያሉትን አሳብ ግራኝ ተቀ
በለ ። ሃይቢም የራሱን አሳብ ለማጽደቅ ቢወተውት ዝም በል ብሎ ገሠጸውና ከዝ
ሆን ዱር (ጅባት) በጉድሩና በእንደገብጣን (ዛሬ አዲስ ዓለም ያለበት) በኩል አድር
ገው ወደሸዋ መጡ ።

የዘረፉ ሀብት እያጓጓው ወታደሩ ወደ አገሩ እንዳይመለስ ለማድረግ ከታለ
መው ፕላን ሌላ ወደሸዋ ለመንዝ ግራኝን ያመራው ዋነኛው ምክንያት የሀብቱ
ነገር ነው ። ኢትዮጵያን በሙሉ ይዤ እገዛለሁ የሚለው ምኞቱ በፊቱ ተደቅኖ ስለ
ሚጠብቀው ይኸን የመሰለውን ምኞት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ የሚያስችለው ገንዘ
ብና ሀብት መሆኑን ተረድቶታል ። የፈረንሳዊ ንጉሠ ነገሥት ናፖሌዎን ጦርነት
ለማድረግ ሦስት ነገሮች ያስፈልጋሉ ፤ አንደኛው ገንዘብ ፤ ሁለተኛው ገንዘብ ፤
ሦስተኛው ገንዘብ ነው ያለው ያን ጊዜ ከግራኝ አህመድ አእምሮ የተሰወረ አይደ
ለም ።

እንደ እውነቱ እስቦ ተጠንቅቆ መሥራቱ ነው እንጂ የሚቸግረው ጉዳዩ ለማ
ንም ምሥጢርነት የለውም ። ወታደርና አለቃን አጣምሮ ማኖር የሚቻለው በገን
ዘብ ነው ። ልዩ ልዩ አዳዲስ መሣሪያ ከነተዋጊው ከቀይ ባሕር ማዶ ማስመጣት
የሚቻለው በገንዘብ ነው ። ዘዴና አስተዳደር ዕውቀት ከተጨመረበት እንደ ገን
ዘብ የልብን የሚያሠራ የለም ። በወጣቱ በግራኝ ሰውነት ውስጥ ሁሉም ዕውቀትና
ችሎታ ፤ ተንኰልና ዘዴ ፤ ጭካኔና ትጋት ለመሪ የሚያስፈልገው ስጦታ ሁሉ በያ
ይነቱ እንደቅመም ተቀይጦ ስለሚገኝ የኢትዮጵያ ነገሥታት አድልበው ባስቀመ
ጡት የወርቅና የልብስ ሀብት በደንብ ለመጠቀም ሲል ንጉሡን ከማባረር መዠመ
ሪያ ሀብትን ማባረር መረጠ ። ሀብቱንም ካገኘ በኋላ የንጉሡ ማባረር ጉዳይ ለጊ
ዜው በሁለተኛ ደረጃ እንዲከተል ስለአደረገ አድራጎቱና አፈጻጸሙ ሁሉ ከጥናት
ጋር የተያያዘ ሆኖ ይገኛል ።

በዚህ ምክንያት በፕላኑ መሠረት ከዝሆን ዱር መልስ የጦር አለቆቹ ጭፍራ
ጭፍራቸውን እየያዙ በየተመደበላቸው ወረዳ ተበታትነው በግድም በውድም የን
ጉሡ ሀብት ያለበትን እናውቃለን እንመራለን በሚሉት ምርኮኞች ወይም አዲስ
ገብ ደጅ ጠኚዎች እየተመሩ አብያተ ክርስቲያናቱን እያቃጠሉ በደብረ ሊባኖስ
በበረሀ ፤ በባደቄ በእንዶጥናህ (የዛሬ እንጦጦ) በቀወት የሚገኘውን የመንግሥትና
የቤተ ክህነት ሀብት ዘረፉ ። ዘራፊዎቹ ወደ ግራኝ ተመልሰው በየበኩላቸው ያገኙ
ትን ከአስረከቡና ለራሳቸው የተመረቀላቸውን ከወሰዱ በኋላ ንጉሡንና ራስ ወሰን
ሰገድን የማባረሩ ጉዳይ ተተክቶ ሁለቱ ያሉበትን በጥብቅ ያሰልሉ ዠመር ።

የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ንጉሡ በበኩላቸው ዋጅ ከራስ ወሰን
ሰገድ ጋር ሳሉ በያለበት ያለው የቤተ መንግሥት ሀብት መዘረፉን ግራኝ አህመድ
በረሀ መኖሩን ሰሙ ። ግራኝም ይኸን ሁሉ ሀብት ከዘረፈ በኋላ ወዳገሩ ለመግባት
ያሰበ መስሏቸው ሳይሄድ አዋሽን ተሻግረው ለመዋጋት ሲሉ ባጠገባቸው ያሉትን

ቊጥራቸው እስከ አርባ የሚደርሰውን ፈረንጆች ባገራችሁ እንደምትሠሩት ያለ ጀልባ ሥሩልኝ ብለው አሠሩ ። ባላገሩንም በሙሉ አዝዘው ፩፻ የሚሆን ለጋ የሚባለው መሻገሪያ ተሠርቶ ሲያልቅ ንጉሡ ከነሠራዊታቸው አዋሽን ለመሻገርና ለመዋጋት ተዘጋጁ ።

ንጉሡ ራሳቸው የበላይ መሪ ሆነው ወደጦር ግንባር ሄደው እንዲዋጉ የታሰበውን ራስ ወሰን ሰገድ አልተስማማበትም ። ስለዚህ በንጉሡና በሹማምንቱ ፊት በእንደዚህ ያለ የጦርነት ጊዜ ንጉሥ ወደ ጦር ግንባር ሄዶ አይዋጋም ። የነገሥታቱም ደንብ አይፈቅድም ፤ እኔው ራሴ አዝማች ሆኜ በርስዎ ፊንታ ከእስላሞቹ ጋር እዋጋለሁ ብሎ አመለከተ ። በዚህ አነጋገሩና አሳቡ ንጉሡም ሹማምንቱም አመሰገኑት ። ስለዚህ በርሳቸው ውስጥ ሆኖ ሊዘምት የተዘጋጀውን የደዋሮን ፤ የጐጃምን ፤ የፈጠጋርን ፤ የዳሞትን ፤ የጉራጌን ፤ የጋፋትን ጦር ሰብስቦ በተለይ ቃርቃራህ በር ወደሚባለው ቦታ መጥቶ ሠፈረ ።

የራስ ወሰን ሰገድ የጦር ዝግጅቱና ውጊያ ከነአሟሟቱ በታሪክ ነገሥቱ ባንድ መስመር የታለፈው በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ ስለተዘረዘረ ዋና ዋናውን ፍሬ ነገር ከዚያው ከዋናው የጽሑፍ ምንጭ ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«ወዚር አዶሌ ከባደቁ ወደ በራራህ (በረህ) ሲመለስ ንጉሡና ወሰን ሰገድ ያደረጉትን ወሰን ሰገድ ጦር ይዞ አዋሽን ተሻግሮ ቃርቃራህ መስፈሩን ለይማም ነገረው . . . . . . ከዚህ በኋላ ይማም ከጦር አለቆቹ ጋር ምክር ያዘ ። ሁሉም አሁን የዝናም ወራት (ክረምት) ስለሆነ ጉዞ የዠመርን እንደሆነ በከንቱ እንደክማለንና ክረምቱ ሲያልቅ እንዋጋለን አሉትና በየሠፈራቸው ተለያዩ . . . . . . ቀጥሎም ሐቀኛ ምክር የሚሰጠውን ገራድ አህሙሹን ለብቻው ጠራና . . . . . ምን ይሻላል አለው ። እርሱም እስላሞቹ ሁሉ የክረምቱን መውጣት ይጠብቃሉ ሲወጣ ሂደን እንዋጋ ይሉሃል ፤ ወደ ጦርነቱ ብቻ ሄደው ጠላትን ያገኙ እንደሆነ ይዋጋሉ ያጡ እንደሆነ ወደ አገራቸው መሄድ ይፈልጋሉና ፍቀድልን ይሉሃል ፤ እሺ ብትል አገራቸው ይመለሳሉ ባትፈቅድም በፈቃዳቸው በየአገራቸው መግባታቸው አይቀርምና አንተ ብቻህን መቅረትህ ነው አለው ። እኮ ታዲያስ ምን ይሻላል ብሎ ቢጠይቀው አቡበከር ቀጢን እስኪመለስ እዚሁ እንቆይ በመጣ ጊዜ ጦሩን ይዞ ሠፈራችንን ይጠብቃል ። ከዚያ እኛ ሄደን እንዋጋለንና በእግዚአብሔር ፈቃድ ንጉሡን የገደልነው እንደሆነ ሕዝቡ በሙሉ እስላም ይሆናል ። የአዋሽ ወንዝም ከዚያ ወዲያ ይሞላልና እስላሞቹ አገራቸው ለመግባት አይችሉም ዝም ብለው እዚሁ ቀርተው ስለዘረፋ ብቻ ያስባሉ ። ሳንዋጋ በመካከል በጋ የመጣ እንደሆነ ግን ከዚያ ወዲያ እስላሞቹን ማገድ በፍጹም አይቻልም ምክንያቱም ኤሚሮቹም ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ወዳገሩ መመለስ ናፍቆታል ብሎ ምክሩን ገለጸለት ። ይማምም አመሰገነውና እንግዲህ አቡበከር እስኪመጣ ይኸን ምሥጢራዊ ምክር ለማንም አታውጣ አለው ። . . . . . ከዚያ ቀጥሎ ኤሚር ሑሴንን ጠርቶ ከገራድ አህሙሹ የተነጋገረበትን ገለጸለት . . . . . ኤሚር ሑሴንም "ጥሩ ምክር ነው ውለህ ሳታድር ነገውኑ ሂደህ ከወ

ለን ሰገድ የተዋጋህ እንደሆነ ትገድለዋለህ ፤ ከዚያም ወዲያ ሀበሻን ትገዛለህ ሁለት ሦስት ቀን ያደርህ እንደሆነ ግን ገራድ አህሙሽ ያለው ይፈጸማል ። የሁሉም እስላም አሳብ ያዘነበለው ወደየአገሩ ለመመለስ ነው” አለው ።

ይኸን ሁሉ ከሰማ በኋላ ይማም ሄዶ ለመዋጋት ቆረጠ ። ኤሚሮቹንም ሁሉ ጠርቶ የሰማሁት ወሬ አለኝና ነገ የፈረሰኛ ፤ የእግረኛ ጦራችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደኔ እንድትመጡ ብሎ አዘዘ ። በማግሥቱ መለከት እያስነፋ ነጋሪት እያስመታ ሹማምንቱ በመጡ ጊዜ ወሰን ሰገድን ለመውጋት አስቤአለሁና ምን ይመስላች ኋል ብሎ ጠየቃቸው እነሱም የኛ አሳብ ክረምት ሲወጣ ለመዋጋት ነበር ፤ አሁን ይህን አዲስ የጦርነት አሳብ ምነው አመጣህብን አሉት እርሱም ዝም በሉ እናንተ አታውቁም እኔ የማደርገውን አውቃለሁ ጠላታችንን የምንወጋው በዚሁ በክረ ምቱ ነው አላቸው ።

ሀብትና ጓዛችንንስ እንይዛለን ወይስ እንተዋለን ቢሉት ይኸ ጉዳያችን አይደ ለም ብሎ መለሰና ወዲያው ወደ አቡበከር ቀጢን ዘወር ብሎ ይህ ያመጣኸው ልብ ስና ዕቃ ያንተ ነው ፤ በዚህ ሠፈር ሆነህ ሴቶቻችንንና ሀብታችንን ጠብቅ ብሎ ፸፱ የፈረሰኛ ወታደር ሰጥቶ ከዚህ አትሂድ ንጉሡ ቢመጣብህ ተዋጋው ታሸንፈውማ ለህ ብሎ አስጠንቀቀውና ይማም የፋቲሃን ድግምት እየደገመ ጉዞውን ዠመረ (1)። ኤሚሮቹም በየፈረሳቸው ወጥተው ተከተሉት ። መንገድ መሪው ከሁሉ ፊት ቀደመ፤ ዝናም ይወርድ ነበር ፤ መንገዱም ሁሉ ጭቃ በመሆኑ ግማሹ ከፈረስ ግማሹ ከበቅ ሎው ይወድቅ ነበር ፤ ሹማምንቱም አንድ ጊዜ ከፈረስና ከበቅሎአቸው እየወረዱ እንዳንድ ጊዜ እየወጡ በፈረስና በበቅሎአቸው ፫ ቀን ተጉዘው ሌሊቱን እክርስቲያ ኖቹ ሠፈር ተጠግተው አደሩ ።

የወሰን ሰገድም ሰዎች መጥተው ይኸው ይማም ከነጦሩ መጥቶ አጠገብህ ሠፍሯል ብለው ነገሩት እርሱም ሐሰት ነው እስላሞቹ በዚህ በዝናምና በጭቃ በአ ረፋ በዓላቸው ጊዜ ጉዞ አይጓዙም ማለትን ሰምቻለሁ አለና ወዲያው ባጠገቡ ያለ ውን ከሐዲ አውራይ ኡስማንን እስላሞች በአረፋ በዓላቸው ጊዜ መንገድ ይሄዳ ሉን በዚህ ከብት በሚያደክም በጭቃስ ይጓዛሉን ብሎ ቢጠይቀው እኔ ቀድሞ በመ ካከላቸው ባገራቸው የነበርሁ ጊዜ በክረምትና ይኸን በመሰለ በዓል ጊዜ አይጓ ዙም ፤ አሁን ግን የሚያደርጉትን አላውቅም ብሎ መለሰ ። ከዚያ በኋላ ሚካኤልና ሮቤል የሚባሉትን ሁለት የደዋሮ አገር ፈረሰኞች አስጠራና ያገሩ ሰዎች ይማም ከነጦሩ መጥቶ እዚህ አጠገብ ሠፍሯል ብለው ነግረውኛልና እስኪ እናንተ ፈረሳ ችሁን ጭናችሁ ሂዱና እስላሞቹ ያሉበትን ስልላችሁ ንገሩኝ ብሎ ላካቸው ። እነ ሱም ለመመርመር በሚጓዙበት ጊዜ ከእስላሞቹ ወገን ደላን የሚባለው ከአራት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ እንጨት ፍለጋ ሲሄዱ ሚካኤል አገኘውና አንተ ሰው እስላም

(1) የፋቲሃ ድግምት የሚለው አንደኛ ማናቸውንም ለማድረግ በስመ አብ ብሎ ጸልዮ እንደመዠ መር ያለ ነው ፤ የቁራንን የመዠመሪያውን ምዕራፍ እንደ መቅድም ሆኖ የያዘው እርሱ መሆኑን ከዚህ በፊት አውስተናል ።

ቹን አይተሃልን ብሎ ጠየቀው እርሱም የምን እስላሞች ቢለው የሚዋጉት ብሎ መለሰ በዚያን ጊዜ ሚካኤል ከላይ ሆኖ ወደታች ቢመለከት የእስላሞችን ሠፈር አየ ። ዳላንንም እስላም መሆኑን ተገንዝቦ ሊሸሽ ሲል ዳላን የበርኖሱን ጫፍ ይዞ ከፈረስ አውርዶት በሰይፍ መታና ማረከው ። ኋደኛው ግን ሸሽቶ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ ። ዳላንም ምርኮኛውን ይዞ ወደ ይማም ወስዶ አቀረበውና አስገደለው ።

ወሰን ሰገድ ሸሽቶ ከመጣው ሰውዬ ላይ የእስላሞቹን በቅርብ መኖር ሲሰማ ጦሩን ሰብስቦ ይኸው እስላሞቹ በኛ ዙሪያ ነውና ያደሩት እንግዲህ ሊጐበኟችሁ መምጣታቸው ነውና ለውጊያ ተዘጋጁ አላቸውና እነርሱ በእንደዚህ ያለ ጊዜ ተዋጉ ብለህ አትዘዘን ብለው ቢለምኑት ታዲያስ ታልተዋጋችሁ ምን ልታደርጉ ነው አላቸው ።እነሱም አንተ የሃይማኖት መሪያችን ነህ አንተ የሞትህ እንደሆነ ሃይማኖታችን ጠፋች ማለት ነው ፤ ስለዚህ ወደ ቦሰት (1) ተራራ እንሂድና በዚያ አንተ እየመራኸን እኛም እየተከተልንህ እስከ መጨረሻችን ድረስ የተዋጋን እንደሆነ የሃይማኖታችን ፍጻሜ አይሆንም ፤ አንተ ግን ከሞትህ ሃይማኖታችንም ይጠፋል አገራችንም ይበዘበዛል ፤ እያሉ አጥብቀው ከፊቱ ቆመው ለመኑትና እሺ አሰኙት ። ከዚያ በኋላ የጦሩን አጋማሽ ለአውራይ ኡስማን ከፍሎ ሰጠውና አንተ ደጀን ሆነህ ጠብቅ ብሎት እርሱ የቀረውን ጦር ይዞ ወደ ተራራው ሲሄድ እስላሞቹ ወደ ክርስቲያኖቹ ሠፈር መጥተው ድንኳኑን ሲያስነቅል በአውራይ ኡስማን ደረሱበት ። እርሱም ጦሩን ይዞ ሳይዋጋ ድንኳኑንና ሠፈሩን ትቶ ሸሸ ። በዚያን ጊዜ እስላሞቹ ወሰን ሰገድ ሠፈሩን ከነሀብቱ ትቶ የሸሸው እኛ ሀብቱን ለመካፈል ስንዘነጋ ድንገት በተንኮል አደጋ ጥሎ ሊዋጋን ነው አሉ ። አንዳንዶቹ የለም በርግጥ ሸሽቷል ሲባባሉ ገራድ ሻሙን ወሰን ሰገድ እሠፈሩ ቢገኝ ግደሉኝ እርሱ በፍጹም ሸሽቶ ወደ አዋሽ ሄዷል ቢል የነዚያን ትቶ የርሱን አመነና ጦሩ ተከፋፍሎ አንደኛው የአውራይ ኡስማንን ሁለተኛው የወሰን ሰገድን ፍለጋ እየተከታተሉ ሄዱ ። ሦስተኛውን ጦር ይማም ይዞ በሌላ መንገድ ሄደ ።

ወሰን ሰገድ እስላሞቹ እንደተጠጉት ባወቀ ጊዜ የብረት አልጋዬን ወንበር ዘርጉልኝ ብሎ እዚያ ላይ ተቀመጠና ነጋሪት እያስመታ ወገኖቹን ለጦርነት ቀሰቀሳቸው ። የደረሱበት እስላሞች ብዙ አልነበሩም ቢሆንም ጦርነቱን ዠምረው አንድ ሰዓት ሙሉ ተዋጉ ። በዚህ ውጊያ ላይ ዋናው ዠግና የፈረሰኛ ተዋጊ ትግሬ አብደላሞተ ። ገዳዩም የጐጃም ነጋሽ ልጅ ነው ። እንደዚህ ሲሆን እስላሞቹ ወደኋላ አፈገፈጉ ። ከኋላ የነበሩት ፈረሰኞች ደረሱና ወዴት ነው የምትሸሹት ደርሰንላችኋልና ወደ ጦርነቱ ተመለሱ አሏቸውና እንደገና ዠምረው እነዚህም አንድ ጊዜ ሲገፉ አንድ ጊዜ ሲሸሹ በመካከል ታላላቆቹ ስመ ጥር የፈረሰኛ ዠግኖች እነገራድ ሻሙን እነ አሊ ኤል ዋራዲ . . . . . እነ አውራይ ኡመር ዲን ፤ እነ ገራድ አቢድ ሌሎችም ሁሉ ደረሱና የሚሸሹትን እስላሞች ማነው እንደዚህ ያባረራችሁ አሏቸው ።እነሱም እለቅዬው (ወሰን ሰገድ) ጦሩን አሰልፎ ገጥሞን አሸነፈን ትግሬውን

(1) ውልንጪቲ አጠገብ ያለው ።

አብደላንም ገደለብን እንደገና አራት አምስት ጊዜ ብንመለስም አልሆነልንም ብለው መለሱ ።

በዚያን ጊዜ ገራድ ሻሙንና አውራይ ኡመር ዲን እንግዲህ ይኸው አሁን ደር ሰንላችኋል ከዚህ ቀደም እንደደረሱላችሁ ዓይነት ያለን አይምሰላችሁ ። ስለዚህ እኛ ከፊት ሆነን እንዋጋለን እናንተ ከኋላችን ተከተሉን ብለው በመዠመሪያ ገራድ ሻሙን የጠላትን ጦር አቋርጦ ገባና ከአዝማቹ (ከወሰን ሰገድ) ወንድም ከገሪማ (ግርማ ?) ጋር ተጋጠመና ክርስቲያኑ በጦር ሊወጋው ሲል ሻሙን በሰይፍ እጁን ከነጦሩ ሰብሮ ከፈረሱ ላይ ገለበጠው ። አውራይ ኡመር ዲንም (የሱልጣን መሐመድ ልጅ) ካንድ በወሰን ሰገድ አጠገብ ከቆመ ሹም ጋር ተጋጥሞ በጦር ወግቶ ገደለው . . . . . . ፥ አል ኤል ዋራዲም ባንድ የክርስቲያን ሹም ላይ ገሥግሶ ተጋጠመና በሰይፍ በትር ጭንቅላቱን ከአንገቱ ቆርጦ ወረወረው ። በዚህ ጊዜ ክር ስቲያኖቹ ማፈግፈግ ዠመሩ ። ወሰን ሰገድም ወዴት ነው የምትሸሹት ብሎ ሲጮ ህባቸው ገራድ አቢድ ወሰን ሰገድን እየሰደበ ቀረበው ወሰን ሰገድም የፈረሱን ፊት ወደ ገራድ መለሰና ተጋጠመው ክርስቲያኑ ጦር እስላሙ ሰይፍ ነበር የያዙት ። ወሰን ሰገድ ለመዠመሪያ ጊዜ አቢድን መትቶ የግራ እጁን አቆሰለው ። እስላሙም ጥሩር ለብሶ ነበርና የጦሩ ጫፍ ከብረቱ ውስጥ ገብቶ ለማውጣት ሲስብ ተሰበረ ከዚያ በኋላ ጦሩን ትቶ ሰይፉን ከአፎቱ ለማውጣት ሲተናነቅ ገራድ አቢድ በሰይፍ ከማዥራቱ ትንሽ ወደ ላይ ከፍ አድርጎ መታው ። ወሰን ሰገድም ከፈረሱ ላይ ወደ ምድር ወድቆ "እኔ ወሰን ሰገድ ነኝ አትግደለኝ አትግደለኝ" አለ ። ክርስቲያኖቹ መውደቁን ሲያዩ ገራድ አቢድም የወደቀው ወሰን ሰገድ መሆኑን ሲረዳ አዝማቻ ቸው ወሰን ሰገድ መሞቱን ለክርስቲያኖቹ ንገሩ ብሎ ለጓደኞቹ ጮኸ ። እነሱም ወሰን ሰገድ ሞተ እያሉ ጮሁ ። እርሱም እንደቆሰለ ተኝቶ ሕያው ነኝ ጦርነቱ ይቀ ጥላል (1) ብሎ ተናገረ ። ክርስቲያኖቹ የአለቃቸውን የወሰን ሰገድን ሞት ሲሰሙ ተዘበራርቀው በየበኩላቸው ሸሹ እስላሞቹም እየተከታተሉ ግማሾቹን እየገደሉ ግማሾቹን ማረኩ ።

ISIC

ይማም በበኩሉ ከዚህ በፊት እንደተባለው በዘቋላ (ዝቋላ) በኩል አድርጎ ሲጓዝ ከወዚር አዶሌ ጋር ተገናኘ . . . . . ። ከዚያ ይማምና ጓደኞቹ ባንድ ቦታ ተሸ ሽገው ሲመለከቱ ከወሰን ሰገድ ጦርነት የሸሸው ጦር ሲመጣ ጓደኞቹ አዩና እነዚ ያው ሸሽተው ይመጣሉና ከፊታቸው ቀድመን እንዋጋቸው አሉ ። ይማም ግን እኛ አራት እነሱ ብዙ ስለሆኑ ትንሽ መሆናችንን ሲያውቁ ተዋግተው ሊገድሉን ይች ላሉ ። ነገር ግን አሳልፈን ከኋላቸው የገጠምናቸው እንደሆነ ያው ያሸነፉቸው ጦር ደርሶ የሚዋጋቸው ይመስላቸዋልና ለኛ መልካም ነው ብሎ ቢመልስ በምክሩ መል ካምነት አመሰገኑት . . . . . ስለዚህ የሚሸሸው ጦር ካለፈ በኋላ ይማም የክርስቲያ ኖቹን አለቃ ገጠመው ፥ ገራድ አህሙሹና አሉሽም እንደዚሁ ሌሎቹን አለቆች እየ

(1) ጽሑፉ አላክን በላ አላክ በላ ሲል (በዛሬው አማርኛ አለሁ በላ አለሁ በላ) ሕያው ነኝ ጦርነቱ ይቀ
ጥላል ማለቱ ነው ሲል ራሱ ዓረብ ፋቂህ ተርጉሞታል ። ገጽ 262 ።

ተዋጉ ገደሏቸው ። አንድ ተክለ ሐዋርያት የሚባል የገኘኑት ስሙ ጉጃም ነጋሽ ንጉሡና ወሰን ሰገድ የሚያከብሩት ነበር ። ከርሱም ጋር ኤሚር ሑሴን ተጋጠሙና ሁለቱም ተናንቀው ኤሚሩ ተክለ ሐዋርያትን ከኮርቻው ላይ ጣለው ፈረሱም ሸሸ ። ኤሚሩም ጦሩን ይዞ ተከታተለና ፈረሱን ይዞ ወደ ክርስቲያኑ ተመለሰ እርሱ ግን እሜካ ውስጥ ገብቶ ቆመ ። ይማም ይኸውልህ አንተ ፈረሱን ስታባርር አለቅ ዪው እሜካ ገባ ብሎ ለሑሴን ነገረው ሑሴንም ይማምም በየተራ ጦራቸውን ቢወ ረውሩ የዛፉን ግንድ ከመምታት በቀር እርሱን አላገኘ አለው ።

ከዚህ በኋላ ሑሴን ከፈረሱ ወርጂ በእግሬ ሄጂ ልግጠመው ቢል ይማም ተው ቆይ ብሎት ሳለ በዚሁ መካከል ሁለት ሰዎች መጡ ያንዱ ስም አቡበከር ይባላል ። እርሱንም ከፈረስህ ውረድና በጦርህ ይኸን ክርስቲያን ውጋው ብሎ ይማም አዘ ዘው ከፈረሱም ወርዶ ተጠግቶት ሁለት ጊዜ በጦር ቢመታው ምንም ሊያደርገው አልቻለም ክርስቲያኑ ግን እጁ ላይ ጅራፍ (ትልቅ አለንጋ ?) ነበርና ወደፊት ተራ ምዶ አቡበከርን በጅራፉ መትቶ ከርሱ በኋላ አርቆ ወረወረው ። ደግሞ ለሁለተ ኛው ሰበርዲን ለሚባለው ውረድና ይኸን ክርስቲያን ግደል ብሎ ይማም አዘዘው ሰበርዲንም ዋና የተፈራ ስመ ጥር የሆነ ባለሰይፍ ወታደር ነበርና ከበቅሎው ወርዶ ባንድ ጊዜ በትር ጣለውና ከዛፉ ውስጥ ጐትቶ አውጥቶ ገደለውና ገፈፈው ።

ከዚያ የቀረውንም የክርስቲያን ጦር ገድለው ምርኮውን ሁሉ ከማረኩ በኋላ . . . . . ሁሉም ወደ ማኅ ተገናኙና ስላገኙት ድል እምላካቸውን አመሰገኑ ። በዚህ ጊዜ ለምን ወሰን ሰገድን እንዳላየው ገደልኸው ብሎ ይማም ገራድ አቢድን ጠየ ቀው ። እርሱም ምን ያደርግልሃል . . . . . . ፤ የተማረከ ጊዜ ወደ ጌታዬ እወስድሃ ለሁ ብለው አንድ ዛፍ ሥር ተኘቶ አደራሁን እዚሁ ጨርሰኝ ብሎ ተማጥኖ ፤ ቢለም ነኝ ገደልሁት ብሎ መለሰለት ።

ከዚህ በኋላ ይማም ምርኮኞቹን አቅርቡልኝ ብሎ አዘዘ ፤ ከምርኮኞቹም ውስጥ አዶሌ የማረከው ዣን ነሃድ የአዳል አንባጅ ገዥ ቃሲም የዣን አሞራ ገዥ ነበሩ ። ቃሲም እስላም ሆኖ ሲኖር በኋላ ክድቶ ለንጉሡ የገባና በትግሬና በአንጎት መካከል የነበረውን ግዛት ተቀብሎ ብዙ ጊዜ በጦርነት እስላሞቹን ያስጨነቀ ሰው ነው ። ከነዚህም ጋር ሐና የላሊበላ ገዥ በጠቅላላው ፴ ሹማምንት ነበሩና ሁሉንም ይማም አስገደላቸው ።

እንደዚሁም ወሰን ሰገድ ድል የሆነ ጊዜ ገብረ እንድርያስ የሚባለው ተማርኮ ነበር ። እርሱም በሀበሻ አገር ከአድማስ (1) ዠምሮ እስከ ወናግ ሰገድ (ልብነ ድን ግል) ድረስ ያልገዛሁት አገር ያልተሾምሁት አውራጃ የለም እያለ ይመካ ነበርና ተገደለ ። በዚህም ጊዜ ዕድሜው ፺ ዓመት ነበር ።

ከወሰን ሰገድ ሞት በኋላ አገሩ ተገዛ የጦር ሠራዊቱም ተዋረደ ፤ ወደፊትም

(1) አድማስ የሚለው ዓፄ በእደ ማርያምን ነው ። እርሳቸውም ያፄ ልብነ ድንግል አያት ስመ መንግሥ ታቸው ዳዊት ነው ፤ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ አድማስ ሰገድ ስለሚባሉ ዓረብ ፋቂህ የተከተለው ይኸ ንን ነው ።

እንደምናነባው ከሕዝቡም አብዛኛው ክፍል እስልምናን ተቀበለ» ሲል ዓረብ ፋቂህ የራስ ወሰን ሰገድን ፍጻሜ በዚህ ዓይነት ያሳየናል (1) ።

ይህ ታላቅ ሰው የሞተበትን ወርና ቀን ዓረብ ፋቂህ አልጻፈውም ነገር ግን ታሪክ ነገሥቱ የደብረ ሊባኖስን ቃጠሎ በሐምሌ ፳፬ ቀን ካደረገ በኋላ የወሰን ሰገ ደን ሞት በነሐሴ ፩ ቀን ያደረገው ትክክለኛ ነው ። ጦርነቱ የተደረገበትን ወራት የክረምት ወራት (ሐምሌና ነሐሴ) መሆኑን ዓረብ ፋቂህ ያረጋገጠው ከዚህ ከታሪክ ነገሥቱ ወርና ቀን ጋር ገጥሟል ።   የተዋጉበት ሥፍራ  ዓረብ ፋቂህ ወደ ቦሰት ተራራ ለመንዝ ቃርቃራ ሳለ ብሎ የጠቀሰውን እነኮንቲ ሮሲኒ ቆርቆራ ብለው ታል ። ይህ ሥፍራ ዛሬ ካዲስ አበባ ሄዶ ቢሾፍቱ ሊደረስ ትንሽ ሲቀር (፫ ኪ. ሜ.) በቀኝ በኩል የሚታየው ቁርቁራ መሆን አለበት (2) ።

ምዕራፍ ፶፫

የራስ ወሰን ሰገድ የአሟሟት ዓይነት - የሕዝቡ በጅምላ መስለም ፤

እነሆ የመጨረሻው ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የራስ ወሰን ሰገድ ጦርነቱና ሕይወቱ በዚህ ዓይነት ተፈጸመ ። ራስ ወሰን ሰገድ የሞተ ዕለት ስመ ጥሩው ገራግና ከ፲፭ ዓመት በፊት ማኅፉዝን የገደለው የዘጠና ዓመቱ ሽሜ፲፫፻ጀ አባ ገብረ እንድርያስ ተማርኮ ሞተ ። ከሁሉ የሚያሳዝነው አሟሟት እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ በንጉ ሡና በራስ ወሰን ሰገድ ዘንድ የተከበረው የጐጃም ነጋሽ ተክለ ሃይማኖት አሟ ሟት ነው ። ዋናው አዝማች ራስ ወሰን ሰገድ ተመትቶ ወድቆ   ጦሩ ፈራርሶ በያለ በት ሲሸሽ ይህ የተከበረው ሰውዬ ያለጭፍራ ብቻውን ሲሸሽ ጊዜ የሰጠው ኤሚር ሑሴን ተናንቆ ከፈረሱ ላይ ጣለው ወደ ጫካም ገብቶ ለመደበቅ ቢሞክር ግራኝና ሑሴን እነሱ በቀጥታ ከርሱ ጋር መግጠም ስለፈሩ የበረታ  ወታደር እየላኩ እዚ ያው እተደበቀበት ጫካ በገዛ አገሩ እንደ አውሬ አስደብድበው አስገደሉት ። የሆነ ሆኖ ተክለ ሐዋርያትም ምንም እንኳን የጦር መሣሪያው በጦርነቱ ሰዓት ከእጁ ቢጠፋበት ወይም ቢወሰድበት በእጁ ላይ በቀረው ረዥርም አለንጋ በጫካው ውስጥ እንዳለ ሊይዙት የቀረቡትን ሁሉ እየመታ ጠላቱን በመጉዳት የቻለውን ያህል ተከ ላከሏል ። ዳሩ ግን ጊዜ ባጋደለበት ሰዓት ማናቸውም ዓይነት መከላከል ከንቱ ነው።

ጦሩ ክሦስት ላይ ተከፍሎ ፩ኛው ከራስ ወሰን ጋር ተጋጥሞ ተዋግቶ ሲሸነፍ ግራኝ ሲል ሁለተኛው ክፍል ደርሶ ባዲስ ኃይል የራስ ወሰን ሰገድን ጦር ሲያሸንፍ ግራኝ በሌላ አቅጣጫ ሄዶ ስለ ነበር ጦርነቱን አልተካፈለም ። በዚህ ምክንያት ከውጊያው በኋላ ይኸን ስመ ጥር የክርስቲያን መሪ ራስ ወሰን ሰገድን ከነሕይወቱ ለማየት ናፍቆት እንደነበረው ጽሑፉ ይገልጻል ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 256 - 267

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 252 የልብነ ድንግል ታሪክ ኮ. ሮሲኒ ገጽ 16 ማስታ. ቍ. 1 ።

ዓረብ ፋቂህ ባንድ ቦታ ላይ መነኰሳት ባንተ እጅ እንደምወድቅ ነግረውኛልና ስትማርከኝ እንድትራራልኝ ብሎ ልኮ ነበር ሲል ከዚህ በፊት ጽፏል ። ምናልባት በዚህ አመካኝቶ የጠላቱን ጦር ለማሰለል ሰው ልኮ ይሆናል እንጂ ራስ ወሰን ሰገድን የመሰለ ትልቅ ሰው የግራኝንም ጨካኝነት የሚያውቅ ክብሩንና ዝግንነቱን ዝቅ አድርጎ የሚያስገምትበትን ይኸን የመሰለ መልእክት ሊዋጋው ለሚዘጋጀው ጠላቱ የሚልክ አይመስልም ። ደግሞ የዚህ የፍርሃትና የመላላት መንፈስ ቢኖረው ኖሮ እንደዚህ አድርጎ ራሱ እየተዋጋ ጦሩንም ሊሸሽ ሲል ወደፊት ነው የምትሸሹት እያለ እየተቆጣ ባላዋጋ ነበር ። ለሕይወቱ ቢሳሳ ኖሮ ጦሩ ሳያልቅበት ከሚሸሸው ወታደር ጋር አብሮ ሸሽቶ ወደ ንጉሡ ዘንድ ለመሄድ በቻለ ነበር ። በዝሆን ዱር ጦርነት ተመልሶ ንጉሡን ሳይረዳ በቀረ ጊዜ ለሕይወቱ የሳሳ ያስመሰለውን በዚህ ቀን ግን በርትቶ መዋጋቱን በደንብ እንመለከታለን ።

ነገር ግን ግራኝና ጦሩ ከአራት ዓመት ዝምሮ በሽምብራ ኩሬ በአይፈርስ አሁን በቅርቡ በዝሆን ዱር እያከታተለ ያገኘውን ድል ስለሚያውቅ በወሰን ሰገድ ልብ ውስጥ ስዋጋ እሸነፋለሁ ፡ እማረካለሁ ፡ እቆስላለሁ ፡ እሞታለሁ የሚል ሥጋትና በዚህ ጐን ደግሞ በርትቼ ብዋጋ እስካሁን ድረስ አሸናፊ የሆነውን ግራኝን በእግዚአብሔር ፈቃድ አሸንፌ ያገሬን ጠላት በመበቀል ሕዝቡ በኔ ላይ የጣለውን እምነት እፈጽም ይሆናል የሚል የድል ተስፋ ጣልቃ እየገባ መንፈሱን ሲያጽናናው እንደሚችል የታ[illegible]ነው ። ወደ ጦርነት የሚሄድ የየትም አገር የጦር አለቃ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በአሳቡ ውስጥ እየተመላለሱ ሁከት መፍጠራቸው የታወቀ ብቻ ሳይሆን የባሕርይ ነው ።

ዳሩ ግን ከነዓዌ ዓምደ ጽዮን ከነዓዌ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር የነበረ የድል አምላክ በዚህ ጊዜ ከግራኝ አህመድ ጋር ስለሆነ ምንም ማድረግ አልተቻለውም ። እነ ራስ እስላም ሰገድ እነአዝማች ተክለ ኢየሱስ እነጸሐፈ ላም ሮቤል በሄዱበት የዝግንነት ጐዳናና ሞት ወሰን ሰገድም ሄደበት ። እንደ ዝግና የጦር አለቃ በፈረሱ ላይ ሆኖ ራሱ በጦር ሰይፍ ይዞ ጥሩር ለብሶ ከገጠመው ባላጋራው ጋር ተደባድቦ ደኅንነኛ አሟሟት ሞተ ። ከመሞቱ በፊት ቆስሎ በወደቀ ጊዜ ገዳዩ ገራድ አቢድ የተዋጊውን ምራል ለመጣል ጌታችሁ ወሰን ሰገድ ሞቷል እያለ ቢለፍ ወይም ቢያስለፍፍ "አለሁ በል ውጊያውን ቀጥሉ" ሲል በሞትና በሕይወት መካከል ባለበት ሰዓት መሸነፍን ተቃውሟል ። ይህ ሁሉ በወገኖቹ ብዕር ተብራርቶ ሳይጻፍ በመቅረቱ ያሳዝናል ። ያለዚያ ብዙ ዓይነት የተሠራ ጀብዱ ባነበብን ነበር ።

ምንም እንኳን ዝርዝር ታሪክ በመስጠቱ ብናመሰግነው ዓረብ ፋቂህ ከጠላት ወገን የሆነ ጸሐፊ መሆኑን አንዘነጋውም ። ይህ ጸሐፊ አሁንም የራስ ወሰን ሰገድን የሕይወት ፍጻሜ ተጻራሪ በሆኑ በሁለት ዓይነት መንገዶች ይገልጸዋል ። አንደኛው ተመትቶ ከፈረሱ ላይ ሲወድቅ እኔ ወሰን ሰገድ ነኝ አትግደለኝ አለ ይላል ። ከዚያ አልፍ ብሎ ደግሞ እንደቆሰለ ባላጋራው በምርኮኛነት ለመውሰድ ሲጐትተው እባክህ እዚሁ ጨርሰኝ ብሎ ባላጋራውን ገራድ አቢድን አጥብቆ እንደለመነውና ተለማኙ ጨርሶ እንደገደለው ይገልጻል ። የዚህም የልዩነቱ ምንጭ ከዓረብ

ፋቱህ ወይም ከነጋሪው ስሕተት ይሁን ወይም በእርግጥ የመገርመሪያው ቁስል
ሳይጸናበት አትግደለኝ ካለው በኋላ ባላጋራው ግን በድጋሚ ክፉኛ አቁስሎት የቁ
ስሉን ጽናት በመገንዘብ ወይም ከነሕይወቱ እግረኛ ፊት ቀርቦ በምርኮኛነት የመ
ታየቱ ውርደት አሰቅቆት እዚሁ ጨርሰኝ ብሎት እንደሆነ በትክክል አይታወ
ቅም ።

ወደ ጦርነቱ ፕላን የተራመድን እንደሆነ አሁንም በክርስቲያኖቹ ዘንድ ባን
ድነት ተሰብስቦ ከልብ ቀርጦ ይኸን ጨካኝ ጠላት በመውጋት ፈንታ ኃይልን በየ
ምክንያቱ የመበታተንና ለጠላት የመመቸት መንገድ በሰፊው ይታያል ።

ባለፈው እንዳነበብነው ለንጉሡ ሕይወት በመሳሳት ራስ ወሰን ሰገድ ንጉሥ
ወደ ጦር ግንባር ሄዶ ማዋጋት የለበትም ስላለ በዚሁ ተመስግኖበት ለራስ ወሰን
ሰገድ ግማሹ ጦር ሲሰጠው የቀረው ከንጉሡ ጋር ተከፍሎ በወጅ ወደ ኋላ የቀረ
አለ ። ደግሞ የቀሩት ሹማምንት ለራስ ወሰን ሰገድ ሕይወት ስለሳሱ ከዚህ ሥፍራ
ወደ ቦሰት ተራራ ሄደን ብንዋጋ ይሻላል እዚህ ስንዋጋ ብትሞት የሃይማኖታችን
ፍጻሜ ይሆናል ስላሉ አውራይ ኡስማን የሚያዝዘው ጦር ተከፍሎ ወደኋላ ከቀረ
በኋላ የራስ ወሰን ሰገድ ቀድሞ ሲጓዝ በዚህ መካከል እስላሞቹ በግሥጋሤ ደርሰው
ራስ ወሰን ሰገድን ሲወጉት ጦርነቱን የአውራይ ኡስማን ጦር አልተካፈለም ማለት
ነው ። ስለዚህ ምናልባት ንጉሡ በደጀን ሆነው እየጠበቁና እያበረቱ ቢያዋጉ
ራስ ወሰን ሰገድና አውራይ ኡስማንም በመለያየት ፲፭፻፴ ግራኝን አለበት ድረስ
ሄደው ቢወጉት ወይም እርሱ ሲመጣባቸው ጸንተው ቢመክቱ ኖሮ ሊያሸንፉት
ይችሉ እንደነበረ ማን ያውቃል ። ወደሌላ ሄደን እንዋጋ ብለው ራስ ወሰን ሰገድን
የለመኑት ሹማምንት የተናገሩት በተዋጊው ወታደር ፊት እንደሆነ ይኸው ራሱ
በቅድሚያ የዝግንነትን መንፈስ ይቀንሳል ።

አባርሮ በአጥቂነት ባላጋራን በመውጋትና የባላጋራን ውጊያ እያፈገፈጉ በመ
ከላከል መካከል ከፍ ያለ የሳይኮሎጂ ልዩነት በተዋጊ መንፈስ ላይ ሊፈጥር ይች
ላል ። በማፈግፈግ መልክ የሚዋጋ ወታደር በአሳቡ የሽሽትና ነፍስን የማዳን መን
ፈስ በግድ ይፈጠርበታል ። በአጥቂነት መስመር የተሰለፈ ወታደር ግን ደካማውን
እንኳ አጥቂ ነህ በርታ በለው እያሉ በሞቀ ንግግር ካበረታቱት ፈሪው ጉልበት ሊያ
ገኝ ይችላል ፡ አልኸኛውም በእልሁ ላይ እልህ ይጨምራል ። ራስ ወሰን ሰገድ አባ
ቶቻችሁ ሲያሸንፏቸው የኖሩት እስላሞች እንዴት አሸነፏችሁ በሚል አነጋገር
የሹማምንቱንና የወታደሩን ሞራል ለማንሣት ከሞከረ በኋላ በአሰላለፍና በመከ
ፋፈል መልሶ የጣለው ይመስላል ።

ከሌላው ችሎታና መሪነት ጋር ግራኝ የሳይኮሎጂ ጦርነት እንደሚያደርግ
ባለፈው ያነበብነውን ለትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ መልሰን እናስታውሳለን።
እርሱና ቊጥራቸው ያነሰ ሹሞች ባንድ ቦታ ተሸሽገው ሳለ ከጦሩ ቦታ እየሸሹ የሚ
ሄዱትን ክርስቲያኖች ባዩ ጊዜ ከርሱ ጋር ያሉት ጓደኞቹ እንግዲህ እንበላቸው
ቢሉት እርሱ ግን ቊጥራችን ያነሰ ስለሆነ ከፊት ስንገጥማቸው ምንም ሸሽዎች
ቢሆኑ እንሰራርተው እኛን ጥቂቶቹን ለማጥፋት ይበቃሉ እነሱን አሳልፈን ከኋላ

የገጠምናቸው እንደሆነ ግን ያው በጦሩ ሚዳ ያሸነፈን አባራሪ ይሆናል የሚል ግምት ስለሚያድርባቸው እየሸሹ ይሞታሉ እንጂ ተመልሰው ከኛ እየተዋጉ ለመሞት አይደፍሩም ያለው ራሱን ከሞት አደጋ ለመጠበቅ ከማሰብ ጋር አስተያየቱ ትክክለኛ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ ግራኝ ፳፯ ዓመቱ ነው ። ይሁን እንጂ በዚህ በወጣትነት ዘመኑ አስተያየቱ የበሰለ ስለሆነ በውነቱ ድሉን እየደጋገመ የሚያገኘው በአዳዲስ መሣሪያና ከውጭ አገር ተሰብስበው በመጡ የዓረብ ፥ የቱርክ ፥ የፋርስ ወታደሮች ተዋጊነት ብቻ ሳይሆን በራሱ የአመራር ችሎታና በአወጋጉ ዘዴ በጦርነቱ ስልት መሆኑን ጭምር ማመን ግዴታ ይሆንብናል ።

የሆነ ሆኖ የራስ ወሰን ሰገድ ሞት በንጉሡ ፥ በጦር አለቆቹና በጦር ሠራዊቱ ላይ ምን ያህል ከባድ ኀዘን እንደሚፈጥር ለመገመት ቀላል ነው ። ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግልም ስላንተ እኔ ሂጂ እዋጋለሁ ያላቸውን በማስታወስ ስለኔ ተሠዋ ብለው የመረረ ኀዘን እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ። ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት በኋላ በፈጠጋር በሸዋ በደዋሮ ያሉት አገራቸውን ንጉሣቸውንና ሃይማኖታቸውን ከልብ የሚወዱት ሁሉ ተስፋ ከመቁረጥና ከጭንቀት የተነሣ እየተሰለፉ ለግራኝ ገቡለት ። እርሱም አውቀው የገቡለትንም በምርኮ ያገኛቸውንም እያሰለፈ በጅምላ አሰለማቸው ። እንገዛለን እንጂ ሃይማኖታችንን አንለውጥም ያሉትን በጦርና በጐራዴ በሰይፍ እያስደበደበ ፈጃቸው ። የርሱን ምሳሌ በመከተል ሹማምንቱ እነወዚር አዶሌ፣ እነአቡበከር ቀጢን ፥ እነኤሚር ሞጋሂድ በየአውራጃው እየተዘዋወሩ ይኸንኑ የአጥቂነት ተግባር ፈጸሙ ።

በዚሁ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈው ሌላው ሁሉ በግድም በውድም ሲሰልም አንድ አይበስ ለሐቲ (አይበስ ለሐዌ) የሚባል በእናቱ ከንጉሡ የሚዛመድ የቀወት ሹም ወታደሩና ባላገሩ ሲሰልም እርሱ ብቻ እምቢ አለ ። እግራኝ ፊት የቀረበ ጊዜ እስላም አልሆንም አባቶቼ አያቶቼ የሞቱበትን የክርስትና ሃይማኖት ለመለወጥ አልመጣሁም ብሎ ተናገረ ። ግራኝም እነዚህ ሁሉ ጭፍሮችህ ሲሰልሙ ያንተ መጽናት ለምንድን ነው ቢሆንም ከነርሱ ትሻላለህ ቢለው እነርሱ የማይረቡ እንስሶች ናቸው ። የራሳቸውንም ሃይማኖት የናንተንም ሃይማኖት አያውቁም ሃይማኖታቸውን ሲለውጡ ውርደት አይሰማቸውም ። አይበስ ለሐዌ ስለመ ተብሎ ለኔ ለንጉሡም ለመኳንንቱም ዘንድ ቢሰማብኝ ትልቅ ውርደት ነውና ሃይማኖቴን አልለውጥም ብሎ መለሰ ።

ከተክለ ሃይማኖት ላይ የተማረከችው የግራኝ ሚስት ሃጂራህ ለዚህ ለሰውዬው ስለምትዛመደው ግራኝም እርሷን ይወዳት ስለነበረ ባንተና በእኛ መካከል ዝምድና አለ ከክርስቲያኖቹም መካከል ትልቅ ሰው ስለሆንህ ወደፊት ታገለግላለህና እምቢታህን ተው ብሎ አጥብቆ ቢጠይቀው ዘመድህ አገልጋይህ እሆናለሁ ነገር ግን ሃይማኖቴን አልለውጥም ከእስላም ወይም ከክርስቲያን ጋር ብትዋጋ ያንተ ረዳት ነኝ ብሎ መልሶ በሃይማኖቱ ጸና ። ግራኝም ዝም በል ለኔ የክርስቲያን እርዳታ አያሻኝም ። ልታገለግልም ልትነዳም አትችልም ይልቅስ ፈረስህንና የጦር

መጣሪያህን አስረክብና ሃይማኖትህን ይዘህ ግብርህን እየገበርህ ተቀመጥ ብሎ በቁጣ ቃል ገላምጦ ተወው ። እንግዲህ ይህ ታላቅ ሰው በሃይማኖቱ እንደዚህ ሲጸና ግራኝ እንደሌሎቹ በሰይፍ አንገቱን ያልቀረጠው የተክለ ሃይማኖት ሚስት የነበረችውና አሁን እርሱ ያገባት ልጅም የወለደችለት ዘመዱ ስለሆነች እርሷን ላለማስቀየም ትቶታል ማለት ነው ።

ከርሱ ከተለያየ በኋላ የሰለሙት የጦር ሹማምንቶች ተሰብስበው ግራኝ ቢተወህ ሌሎቹ ሕይወትህን አይምሩትም ያውስ ሃይማኖቴን አልለውጥም የምትለው ከኛ በልጠህ ነውን ይልቅስ ስለምና ከኛ ጋር ተቀመጥ አለዚያ አንድ ተንኮል ሠርተን እኛው እናስገድልሃለን ብለው እንደገና ስለአስፈራሩት ሰለመና ፫ ወር ከግራኝ ጋር እንደተቀመጠ በኋላ ጊዜ ሲመቸው አምልጦ ወደ ንጉሡ ሄዶ ክርስቲያንነቱን አጸደቀ ።

በዚህ ዓይነት ግራኝ በደብረ ብርሃን (ተጉለት) ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ እነ ገራድ ናስርን እነገራድ አቢድን እየላከ አገሩን ሁሉ አሰለመ ። የቀረው ሁሉ ሲሰልም እምቢ ያሉት ሁለት ሹማምንቶች ከነጭፍራቸው ገራድ ናስር ይዟቸው ወደ ግራኝ ዘንድ አምጥቶ አቆማቸው ። ግራኝም አገሩ ሁሉ ሲሰልም የእናንተ እምቢታ ምንድን ነው ብሎ ቢጠይቃቸው ያለንበትን ሃይማኖት ልንለውጥ አልመጣንም የመጣነው ስለሃይማኖታችን አንገታችንን ለማስቆረጥ ነው ብለው መለሱለት በዚህ መልስ ግራኝ ተገረመ ። ዳሩ ግን የርሱ ምኞት አገሩን ሁሉ በሙሉ ማስለም ስለሆነ በመንፈሳቸው ጽናት ብቻ ከመገረም በቀር ምሕረት ሊያደርግላቸው አልፈለገምና ደግ ነው ብሎ ወዲያው አስገደላቸው (1) ።

ስለዚህ ይኸን በመሰለ ሁኔታ ያን ጊዜ የነገሥታቱ መቀመጫ የነበረውንና ምርጥ ተዋጊ የሞላበትን የሸዋን ፡ የፈጠጋርን ፡ የደዋሮን ፡ የበረህን ፡ የደዋሮን ፡ የባሌን ፡ የወጅን ፡ የኢልማያን (አሩሲ) አገር እያሰለመ የገኘኸነት ሥልጣኑን በነዚህ አውራጃዎች ላይ አረጋገጠ ፣ ላስተዳዳሪነትም በየአውራጃው የራሱን ሹማምንት እያደላደለ አከፋፍሎ ሾመ ። ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ ተስፋ ሳይቆርጡ እነ አዝማች አዳሉም በባሌ እንደገና ቢዋጉም የልባቸውን ዝግጁነት እየፈጸሙ ሕይወታቸውን ላገራቸው ከመሠዋት በቀር የግራኝን ሥልጣን ከወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ ሊያነቃንቁት አልቻሉም ።

እንግዲህ ወደፊት ባለው ጊዜ ውስጥ የምንመለከተው በሸዋና በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን አገር ከገዛና ሀብት ከሰበሰበ በኋላ የንጉሡን ዱካ በመከተል ጨካኙ ግራኝ በወሎ ፣ በትግሬ ፣ በበጌምድርና በጐጃም ያደረገውን ጦርነት ነው ። በዚህ መካከል በሰፊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ሹማምንት አልፎ አልፎ ከዳተኛና አድር ባይ ባይጠፉም አብዛኞቹ ያለፉ ድልና አልቂት ተስፋ የማያስቆርጣቸው እሉ ። እነዚህም የግራኝ ሥልጣን በቆየበት በ፲፭ቱ ዓመት ውስጥ ትግላቸውን ያለ ዕረፍት ሲቀጥሉ በየምዕራፉ እንመለከታለን ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 269 - 272

## ምዕራፍ ፶፩
## በዚህ ዘመን የዓለም ሁኔታ ባጭሩ — ፖርቱጋል ለእርዳታ ፈጥኖ ያልደረሰበት ምክንያት ።

ዓፄ ልብነ ድንግልን ይኸን የመሰለ ጦርነት ገጥሞ በሚያዋክባቸው ጊዜ የዓለም መልክ ከምን ላይ እንደነበረ በጨረፍታ ለመመልከት ያህል የፈለግን እንደሆነ አጭር ሁኔታው ከዚህ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን ። ግማሹ ዓለም በጦርነት ሲቸገር የቀረው በመዝናናት ፤ በጋብቻ ፤ በሃይማኖት ሲጣላ ሲታረቅ የቀረው በጉኑ ያለውን እየወጋ ግዛቱን ሲያስፋፋ ይታያል ።

ሀ. በእንግሊዝ አገር ሔንሪ ስምንተኛ (HENRY VIII) ፈረንሳዮችን በ፲፭፻፲ ዓ. ም. እንደ እው. ቀ. በጊኒጋት ካሸነፈ በኋላ ከፈረንሳዊ ንጉሥ ከፍራንሷ ፩ኛ ባላጋራ ከሻርል ፭ኛ ጋር በመስማማቱ የቀድሞ ሚስቱን ካቴሪን ዳራጎን የምትባለዋን ፈትቶ ሐና ቦሌይን ለማግባት ፈልጎ ይኸ ድጋሚ ጋብቻ በሮማ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ክልክል በመሆኑ በንጉሡና ጋብቻውን በከለከሉት የሮማ ሊቀ ጳጳስ በቀሌምንጦስ ዘንድ ከ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ጀምሮ ከፍ ያለ ጠብ ሆኖ ካቶሊካዊው የእንግሊዝ ቤተ መንግሥትና የሮማ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነታቸውን አቋርጠው በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ንጉሡ በጳጳሱ የተወገዘ ሆኗል ።

ለ. ሻርል ፭ኛ የሚባለው ከጀርመንና ከኤስፓኝ ከሁለት የነጋሥያን ዘር በመወለዱ ግዛቱ በጀርመንና በነምሳ በኤስፓኝ በቤልዥግ በኢጣልያ ሰሜን ተስፋፍቶ የፈረንሳዊን ንጉሥ ፍራንሷ ፩ኛን በሚላን ላይ አሸንፎ በምርኮ ወደ ማድሪድ ከላከው በኋላ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ለመንገሥ ስለፈለገ የሮማው ሊቀ ጳጳስ ባንድ ወገን ለፈረንሳዊው ንጉሥ በማድላት በሌላው ወገን የጀርመኑ ንጉሥ በዚህ ዘመን የሮማ ቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርና ልማድ በዘጠና አንቀጽ ነቅፎ የተነሣውን ማርቲን ሉተርን ስለሚደግፍና በንጉሡ ነገሥትነት አልቀባህም ስላለው በዚህ ሁለቱ ተጣልተው የሻርል ወታደሮች ሮማን ወርረው ዘርፈዋታል (1) ።

ሐ. የፈረንሳዊው ንጉሥ ፍራንሷ ፩ኛ ከሻርል ፭ኛ ጋር በኢጣልያ አውራጃዎች ገዥነት ስለተጣሉና ጥሉም እየባሰ ስለሄደ የጀርመኑ ንጉሥ በሰፊው ግዛቱና ኃይሉ አጥብቆ ስለተጫነው የፈረንሳዊው ንጉሥ ባላጋራውን ሻርልን ለማጥቃት በሮማ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ ጭምር ከእስላሙ ከቱርኩ ሱልጣን ከሶሊማን ጋር ተስማሙ ። ነገር ግን በመጨረሻ በኢጣልያ ግዛት ከሻርል ጋር ጠቡ የማይሆንለት ስለሆነ ዓፄ ልብነ ድንግል ሽምብራ ኩሬ በተዋጉበት እ. አው. ቀ. በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ከሻርል ጋር በካምብራይ ላይ በእርቅ ተስማምተው በውል የኢጣልያ ግዛቱን የፈረንሳዩ ንጉሥ ለጀርመኑ ለቀቀለት ። ከዚህ በኋላ ባመቱ በ፲፭፻፴ ዓ. ም. የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሻርል ፭ኛን በንጉሠ ነገሥትነት ቀብተው አነገሡት ።

(1) Histoire des Papes - F. Hayward 1953 ገጽ 302 - 308

ሠ. በዚህ መካከል ሰሊም ፩ኛ የመካከለኛውን ምሥራቅና ግብፅን በ፲፭፻፲፯ - ፲፰ ዓ. ም. ላይ አስገብሮ ከሞተ በኋላ ልጁ ሶሊማን በባልካን ግዛቶቹን እያስ ፋፋ መጥቶ ሆንግሪንም ከዚያ በኋላ በዚሁ በ፲፭፻፳፫ - ፳፬ ዓ.ም. ላይ በ፫፻፶፰ ወታደሮች የነምሳን ከተማ አስከብቦ ስላስጨነቀ የቀድሞው ጳጳስ ቀሌምን ጦስ የፈረንሳዊውን ንጉሥና የቱርኩን ሱልጣን በሻርል ላይ ለማስማማት የወ ጠኑት ፖለቲካ ተለውጦ አሁን ግን ለማናቸውም የቱርክ እስላማዊ መንግ ሥት የአውሮፓን ክርስቲያናዊ መንግሥት ለመገልበጥ ስላስፈራ የአሁኑ ሊቀ ጳጳስ ጳውሎስ ፫ኛ የፈረንሳዊውን ንጉሥ ፍራንሷ አንደኛንና ንጉሠ ነገሥቱን ሻርልን በሶሊማን ላይ እንዲተባበሩ አስታረቋቸው ። ሶሊማን ከፈረንሳዊ ንጉሥ ጋር ተባብሮ ሻርልን ከኢጣሊያ ምሥራቃዊ ክፍልና ከአፍሪካም ግዛት አስወጣለሁ ብሎ ሲጠባበቅ የቃል ኪዳን ጓደኛው ክርስቲያኑ የፈረንሳዊው ንጉሥ እርሱን ከድቶ ከባላጋራው ጋር በጳጳሱ አማካይነት ታርቆ መደረቡን ሰማ ። ቢሆንም ብቻውን ከወዲህ ወገን በሻርል ውስጥ የነበሩትን የቬኔሲያን ወታደሮች አሸንፎ የሞልዳቪን መስፍን አበረረና ግዛቱን አስፋፋ ። የክርስቲ ያኖች መጠጊያና የመርከብ መተላለፊያ የነበረችውን የሮዶስን ደሴት በኃ ይል ያዘ ። ከሆንግሪ ንጉሥ ከሉዊዝ ጋር ተዋግቶ አስገበረ (1) ።

ሠ. እነዚህን አልፈን አሳባችንን ወደ መስከብ ብናቀና ባስልዮስ የሚባለው ንጉሠ ነገሥት ፖሎኝን ለማስገበር የሚዋጋበትን ጊዜ ፤ ወደሩቅ ምሥራቅ ብንመለ ISIC ከት ቻይና ከሞንጎል ገዥነት ተላቆ የራሱን ገዥነት መሥርቶ በውስጡ የየአ ውራጃው መስፍን እንደባላጋራ እየተያየ እርስ በርሱ ስለሚዋጋ ከ፲፮ኛ መቶ ዓ.ም. ጀምሮ ለምዕራባውያን መግቢያ መንገድ መክፈቱን የቀሩትም የሩቅ ምሥራቅ አገሮች እንደዛሬ ስለአልሰለጠኑ አውሮፓውያኖቹ ፤ ፖርቱጋሎች ሆላንዶች ፤ ኤስፓኞች ቀጥሎም ፈረንሳዊዮችና እንግሊዞች በየአለበት አው ራጃዎቻቸውንና ወደቦቻቸውን የንግድ ጥቅማቸውንም እንደተቀራመቱት እንገነዘባለን ። ይህ

ረ. ከሁሉ የበለጠ እኛ ልንመለከት የሚገባን ስለፖርቱጋል ሁኔታ ነው ። ይህ መንግሥት በ፪ኛው ክፍል እንዳነበብነው በሕንድ ፤ በብራዚል ፤ በአፍሪካ ፤ በሞዛምቢክ ፤ በአንጎላ ፤ በኮንጎ እስከ ደቡብ ግዛቱን ከአስፋፋ በኋላ በቀይ ባሕር መገርመሪያ የግብጾችን ቀጥሎም የቱርክን መርከበኞች እያሸነፈ እ. አው. ቀ. በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. መልክተኞቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከንጉሡ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ተገናኝተዋል ። እነሱም በኢትዮጵያ ፯ ዓመት ቆይ ተው የዓፄ ልብነ ድንግልን ደብዳቤ ለልጁ ለዮሐንስ ፫ኛና ለሮማው ሊቀ ጳጳስ ከወሰዱ በኋላ በቶሎ መልስ ለማምጣትና ንጉሡ በቃልም በደብዳቤም የተስማሙበትንና የተመኙትን ጉዳይ ፖርቱጊዞቹ ሊፈጽሙ አልቻሉም ።

(1) Soliman le magnifique - Fair Fax Downey - trad. S.M. Cuille Min. ምዕ III-IV:

ንጉሠ ነገሥቱ ያሁኑ የጦርነት ችግር ቀይም ብሎ ስለተሰማቸው የፖርቱጋል ጦር በኢትዮጵያ ወደቦች መሸጎ ተቀማጭ እንዲሆንና ራሳቸው ስንቅና አስፈላጊ ውን ነገር ሊሰጡ ፥ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በዚያው ቀበሌ ባለው የእስላም አገር ችና ደሴቶች ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ እንዲያስተምር ተስማምተው ነበር ። ዳሩ ግን ይኸ ንን ምኞታቸውን የፖርቱጋሉም ንጉሥ በሕንድ ያለውም የንጉሡ እንደራሴ ጉዳ ዩን በቅርብ ተከታትለው ከፍጻሜ ለማድረስ አልቻሉም ። ሁሉቱንም ከኢትዮጵያ ጉዳይ የበለጠ ሌላ የሚያባክናቸው የአውሮፓ የሕንድና የብራዚል የቅርብ ጉዳይ ስለሞላ በወዲህ ያለውን የኢትዮጵያን ጉዳይ ችላ ብለውታል ።

በአባቱ በአማኑኤል እግር የነገሠው ዮሐንስ ፫ኛ የንጉሡ ነገሥቱን የሻርልን እኅት ስለሚያገባ ንጉሠ ነገሥቱ ከፈረንሳዊ ንጉሥ ከፍራንሷ ፩ኛ ጋር በሚጣላበት ጊዜ ወገንነቱን ወደ ጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ማድረግ ግዴታ ነበረበት ። ከጐኑ ያለው የኤስፓኝ መንግሥት የቀሩትም የካቶሊክ ነገሥታት እንደሚያደርጉት ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣን እየተቀበለ የካቶሊክን ሃይማኖት በየሰፋፊው ግዛቱ ላይ ማስፋፋት በግዛቱ ያሉት ይሁዲዎችና እስላሞች ክርስትናን እንዲቀበሉ እምቢ ያሉት ከግዛቱ ከፖርቱጋል እንዲነቀሉ በማሠር በመፍታት በማሳደድ ላይ ይገኛል ።

ስለዚህ ዮሐንስ ፫ኛም ሊቀ ጳጳሱም ምንም በአባ ጸጋ ዘአብና በነአባ አልቫ ሬጽ አማካይነት ከኢትዮጵያ ንጉሥ የመጣው መልእክት ቢደርሳቸው በዚያው በቅርባቸው የራሳቸው[illegible]ጉዳይ በቀጥታ ለሚመለከተው ለአገራቸውና ለሥልጣና ቸው ጉዳይ ያስባሉ እንጂ ለኢትዮጵያ አበክረው አያስቡም ። አንዳንድ ጊዜ ጉዳዩ ትዝ ቢላቸውም ለጊዜው በአገሩ ርቀት በመመላለሻው ችግር በጉዳዩ ታናሽነት የተነሣ የአሳብ ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ መልሰው ስለኢትዮጵያዊው ንጉሥ ውድቀት ለጊዜው ምንም ዓይነት እርዳታ ለማድረግ አይችሉም ። ቢያስቡም በአ ሁኑ ሰዓት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የቱርክ መንግሥት በባልካንና በመካከለኛው ምሥራቅ ኃይሉና ሥልጣኑ ጠንክሮ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያለው የግብጽና የዓረብ አገር ሁሉ በርሱ ቍጥጥር ውስጥ ስለተዘጋ የእርሱን ቍጥጥርና ኃይል ጥሶ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ገና ጊዜው አልደረሰም ። ምናልባት ያዒ ሱብን ድንግል በሽ ምብራ ኩሬና በየጦሩ ግንባር በግራኝ አህመድ መሸነፋቸው ወሬው ገና እንኳን በሊስቦን ፥ በሕንድም አልተሰማም ይሆናል ።

በዚህም ላይ አምባሳደር ሆኖ የተላከው አባ ጸጋ ዘአብ ወደፊት እንደምንረ ዳው የተላከበትን ጉዳይ ወትውቶ ወደፍጻሜ አድርሶ በቶሎ እንደተቻለው በመመ ለስ ፈንታ እዚያው ሊስቦን ተቀምጦ ለአምባሳደርነቱ የተገባውን መስተንግዶ እያ ጣጣመ ያገሩን ጉዳይ ችላ ብሎ አገሩ በጦርና በመከራ ሲሰቃይ እርሱ ዝም ብሎ ደስ ታውን ያይ ስለነበረ በዚሁ ዓይ ልብነ ድንግልም ጦርነቱ በበዛበት በ፲፭፻፵፩ - ፵፪ ዓ.ም. በጸጋ ዘአብ ላይ ተናደው እንደነበረ ቤርሙዴዝ ያረጋግጣል (1) ። በ፲፭፻፵፫

(1) Histoire du Christianisme d'Ethiopie... La Croze. Relation du patriarche Bermudez Livre II. ገጽ 95 - 100

(፲፭፻፳፮) ዓ. ም. የፖርቱጋሎቹ መልክተኞች ወዳገራቸው ሲመለሱ ዮሐንስ ቤር
ሙዴዝ ከጓደኛው ከዳ አብሬው ጋር በኢትዮጵያ መቅረቱ ትዝ ይለናል ። ስለ
ዚህ የጸጋ ዘአብ በሊስቦን መቆየቱና ችልታው ያናደደው የኢትዮጵያ የክርስቲያን
ሕዝብ መከራና ሥቃይ ያሳዘነው ከወገኖቹ ተለይቶ ቀርቶ ሁሉንም ዓይቶ የነበረው
ይህ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ ከኢትዮጵያ ሊስቦን ከሊ
ስቦን ሮም በግሥጋሤ ሄዶ ጉዳዩን ቀስቅሶ እነዚያን ፬፻ የፖርቱጋል ወታደሮች
በ፲፭፻፴፬ (፲፭፻፵፩) ዓ. ም. ይዞ ባዔ ገላውዴዎስ ጊዜ እስከመጣ ድረስ ዓፄ ልብነ
ድንግልና የጦር አለቆቻቸው ካህናቱና ሕዝቡ ፤ ሴቱም ወንዱም ወደቡ ሁሉ
ታጥሮ በተዘጋ ቤት እየተደበደቡ ይኸን የጦርነትና የመከራ መስቀል እነሆ ብቻቸ
ውን ለመሸከም ግዴታ ሆኖባቸዋል ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለዚሁ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ ፫ኛ በጻፉት ደብዳቤ
ውስጥ ከአውሮፓ የክርስቲያን ነገሥታት እስካሁን ተዋውቄ በነርሱ ልጅናና አል፰
ልሁም ። እነርሱም እየተጣሉ እርስ በርሳቸው ትልቅ ጦርነት ያደርጋሉ ። ደግሞ
ይበልጥ የማዝነው ከነዚህ ከአውሮፓ ነገሥታት ጋራ መራራቃችን ነው ። በግዛቴ
ውስጥ አንድ የክርስቲያን ንጉሥ ቢኖር ኖሮ በደስታ ከርሱ ጋር በጓደኝነትና በወን
ድምነት እንኖር ነበር ብለው የጻፉት ትክክለኛ ነው ። እነርሱም እርስ በርሳቸው
ትልቅ ጦርነት ያደርጋሉ ያሉት በወሬ የሰሙትን ከዚህ በላይ የጠቀስነውን የጀርመ
ንና የኤስፓኙ ንጉሠ ነገሥት ሻርል ፭ኛና የፈረንሳዊ ንጉሥ ፍራንሷ በፓቪያ
ISIC
(ኢጣልያ) በ፲፭፻፳፭ - ፳፯ ዓ. ም. የተዋጉትን ሳይሆን አይቀርም ። በእርግጥም እን
ደዛሬው ሁሉ ያን ጊዜም ከኢትዮጵያ ጋር የሚዋሰን አንድም የክርስቲያን መንግ
ሥት የለም ። ይኸም እንደ ዕድል ሆኖ በጥንት ታሪክ ውስጥ ኢትዮጵያ ግብፅ ኑብያ
በተዋሕዶ ሃይማኖት ተሣስረው እንደ ወንድማማች ሊሆኑ የሚገባቸው ከ፯ኛውና
ከ፰ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ወዲህ ከዓረቦች ወረራ በኋላ ተዋሕዶዊቱ ግብፅ በዘ
መን ብዛት አብዛኛው ሕዝብና መሪዎቹ ስለሰለሙ በሃይማኖት ልዩነት ብቻ የቀ
ድሞ ዘመን ወንድም የኋላ ባላጋራ ሆኗል ።
የኑብያ መንግሥትም በዘርም በተዋሕዶ ሃይማኖትም ከኢትዮጵያ ጋር ወንድ
ምነቱን አጽንቶ ሲኖር በ፲፬ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ በግብጽ ጦር ተወርሮ ሕዝቡ ስለ
ሰለመ በአሁኑ ሰዓት እንደሌሎቹ አገሮች ሁሉ በቱርክ ሥልጣን ውስጥ ገብቶ ቅኝ
አገር ሆኗል ። ብዙም ጊዜ ከቱርክ ሡልጣን ግብጽን ለማስተዳደር የሚሾመው ፓሻ
ኑብያንም (ሱዳንንም) ደርቦ ስለሚገዛው ለኢትዮጵያ በዚህም በምዕራብ በኩል
ምንም የእርዳታ ጭላንጭል አይታይም ።
ሆኖም የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻውንም ቢሆን እስከዚህ ግራኝ እስከተነሣ
በት ድረስ የራሱን ሃይማኖት የራሱን ነፃነት ይዞ ተከብሮ ይኖር ነበር ። የአክሱምን
መንግሥት ገልብጣ የነገሥታቱን ዘር አስፈጀች ከምትባለዋ በዘጠነኛው መቶ
ዓ. ም. ከተነሣችው ከዮዲት ዝምሮ እስከ ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ድረስ የኢትዮጵያን
ንጉሠ ነገሥት ተዋግቶ ለመጣል ከውጭም ጠላት መጥቶበት አያውቅም ። ከውስ

ጥም በየጊዜው የሚነሡትን የወላስማ ተወላጆች ነገሥታቱ ሁል ጊዜ ድል እየመቱዋቸውና እያስገበሯቸው ይኖሩ እንደነበረ ደጋግመን አመልክተናል ። አሁን ግን በዓለም መንግሥትም የግል ሰውም ሁሉም እንዳማረበት ዘመኑን የሚፈጽም ስለሌለ ሳይታሰብ የግራኝ አህመድ ጦር የንጉሡ ነገሥቱን ጦር አሸነፈ ። ለጠላት ወረራ እንግዳ የሆነችውንም ኢትዮጵያን በያለበት ወረረ ። ወረራውም እስካሁን የደቡቡን ክፍል ይፋትን ደዋሮና ፈጠጋርን ባሌን ፤ ሸዋን ካጠቃ በኋላ የኢትዮጵያን ማዕከላዊና ሰሜናዊ ምዕራባዊ አውራጃዎች አማራ ሳይንትን ቤተ አምሐራን ጐጃምን ፤ ቤገምድርን ፤ ላስታንና ትግሬን ሁሉ አልማረም ።

ዓፄ ልብነ ድንግልና ግራኝ አህመድ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ገጥመው ግራኝ አሸንፎ ንጉሠ ነገሥቱ ተሸንፈው ከተለያዩ በኋላ የግራኝም ማሸነፍ የንጉሡም መሸነፍ ሁለቱንም ሳይገርማቸው አይቀርም ። ግራኝም ድሉ የተገኘው በአላህ እርዳታ ነው ሲል ክርስቲያኑም ንጉሥ በአባቶቼ ያልደረሰው መሸነፍ በኔ የደረሰው እግዚአብሔር ቢጣላኝ ነው ማለታቸው የታወቀ ነው ። ቆይቶ ደግሞ ከአሥር ዓመታት በኋላ ባዬ ገላውዴዎስ የስደት መንግሥት ዘመን ከግራኝ ጦር ይልቅ የሠለጠኑ ፖርቱጋሎች መጥተው ጦርነቱን ሲካፈሉ ተሸናፊና አሸናፊ ቁጣና ምሕረት ሥፍራቸውን ሲለዋወጡ ይታያሉ ።

የሆነ ሆኖ በዚህ ጦርነት ምንም እንኳን ንጉሡ ድል ቢሆኑና ብዙ መኳንንት ቢያልቁም ሌሎች የ[illegible]አለቆች ራስ ደገልሃን ፤ የሠራዊው ገዥ ተስፋ ልዑል ሌሎችም እነራስ ነቢያት እነቢትወደድ ሠርፄ እነአዝማች አዳሉ ወደፊት ታላላቅ የዠግንነት ሞያ እየሠሩ ሲሞቱ የቀሩትም ከንጉሣቸው ጋር ካውራጃ ወዳውራጃ እየተሰደዱ መከራውን በትዕግሥት ሲሸከሙ ፤ ለግራኝም ሁሉ ሲሆንለት በሹማምንቶቻቸው መከባከብ የተነሣ ንጉሡን መማረክ ብቻ ሲያቅተው እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፶፰

### የአውራይ ኡስማን ወደ ግራኝ መግባት (መስከረም ፲፭፻፳፱ ዓ. ም.) —

የራስ ወሰን ሰገድ ሞት ተስፋ እያስቆረጣቸው ወደ ግራኝ እየገቡ የቀድሞ ጌታቸውን ንጉሡን ዓፄ ልብነ ድንግልን ተመልሰው ከወጉት ውስጥ አንደኛው አውራይ ኡስማን ነው ። ኡስማን በሚባለው ስሙ ላይ አውራይ ስለተጨመረ ከክርስቲያኖች በመጣላት ከትግሬና ከላስታ ወደ ሐረር የሾረው የበለው ወይም የረጃ ነገድ መሆኑን በነርሱ ነገድ ወንድ ልጅ ሲሆን አውራይ ሴት ልጅ ስትሆን ባትያ (በዓትያህ) እየተባለች እንደምትሰየም ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ሙሴ ረኔ ባሴት በዚሁ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ሲያብራራ አውራይ (ወይም ኡራይ አውራ ?) ትርጓሜው በበለው ነገድ ዘንድ ነቢይ ወይም የተቀደሰ ማለት ይመስላል ። ባቲያ ወይም ባቲ ደግሞ ወጣት ሴት እንደማለት ነው ብለዋል (1) ። ስለዚህ አውራይ የሹመት ስም ሳይሆን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 255 ማስታወሻ ቁጥር 1 ።

ራችን የትልቅ ሰው ልጅ ሲሆን ልጅ እገሌ እየተባለ እንጂ በነጠላው እገሌ ብሎ እንደማይጠራ ይመስላል ። ባገራችን ለወንድ "ልጅ" የሚባለው ስያሜ ስም ላይ እየተቀጠለ ሲሰጥ ለሴት ልጅ ላገባችው "ወይዘሮ" እንደሚባለው የበ ው ነገድ ሴቷን ባቲያ ወይም ባቲ ይላል ማለት ነው ። በመቆየት ብዛት ግን አው ይ የወንድ ባቲያ የሴት መጠሪያ ስም መስሎ ይታያል ። ምናልባት አውራይ ባገ ችን አውራ (የወንድ አውራ) ከሚባለው ጋር ግንኙነት እንዳለው አይታወቅም ። ዚህ ዓይነት የግራኝ አህመድ ባለቤት ባቲያ ድል ወንበራ የነዚሁ ወገን ነች ገለት ነው ። ከግራኝ ባለሥልጣኖች ውስጥም ከመጠሪያ ስማቸው በፊት "አው ይ" የሚጨምርላቸው እነ አውራይ አቡን የበለው ነገድ መሆናቸው ነው ።

ዓረብ ፋቂህ የአውራይ ኡስማን ሙሉ ስሙ ከነአባቱ አውራይ ኡስማን ነን ዳርአሊ መሆኑን ይኽም ሰውዬ በሱልጣን መሐመድ (መሐመድ የሰዓዲን ኣጅ) ጊዜ ከጦርነት ቦታ ላይ ተማርኮ ክርስቲያን ሆኖ ለንጉሡ የጦር አለቃና የይ ቶት አገር ገዥ መሆኑን ይገልጽና እልፍ ብሎ ደግሞ የኤሚር ፈራቃሃም አሊ (ዋና የግራኝ የጦር አለቃ) ሚስት የአውራይ ኡስማን እኅት እንደሆነች ስለሚናገር ኡስ ማን በርግጥ እስላም የነበረ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም (1) ። በምርኮ ከመጣ ወዲህ ክርስትና ተነሥቶ በፊት ፈጠጋርን ቀጥሎ ይፋትን ተሾሞ ሲያስተዳድር ቆይቶ በባ ደቁ ጦርነት ጊዜ የፈጠጋር ገዥ እንደነበረ በዚያው ምዕራፍ ላይ ተመልክቷል ። የግራኝ ጦርነት ከተጀመረ እንሥቶ በዚህ በአራት ዓመት ውስጥ ለንጉሡ ታማኝ የጦር አለቃ ሆኖ ከግራኝ ጦር ጋራ ብዙ ጊዜ መዋጋቱን ባለፉት ምዕራፎች አንብበ ናል ። ዋና የተዋጋባቸውም ሥፍራዎች ባደቁ ሽምብራ ኩሬ በረህ ፤ ዝሆን ዱር ናቸው ። አሁንም በመጨረሻው ራስ ወሰን ሰገድ ለውጊያ በጦር ሠራዊቱ ምክር ወደ ቦሰት ተራራ በሚገዝበት ጊዜ ከኋላ የጦሩ ደጀን መሪ ሆኖ እንዲያዝ የተመደ በው አውራይ ኡስማን እንደነበረ አንብበናል ።

እኛ በአጻጻፋችን ወገናቸውን ከድተው ለግራኝ የገቡትን እነወናግ ዣንን ፤ እነአዝማች ሃይቢን ፣ እነእናንያን ከሐዲዎቹ እንደምንላቸው ዓረብ ፋቂህም አው ራይ ኡስማንንና እርሱን የመሳሰሉትን በንጉሡ የጦር ግንባር ሆነው የሚዋጉትን የእስላም ሹማምንት የሚጠራቸው በዚሁ በመጥፎ ቅጽል ከሐዲዎች እያለ ነው ። ወደ

አሁን የመጨረሻው ተስፋ ራስ ወሰን ሰገድ በሞተበት ጊዜ ንጉሡ ከወጅ ወደ ቤተ አምሐራ (ወሎ) በሚጓዙበት ጊዜ እንኳን እስላም የነበረው የሐረር ተወላጅ እርሱ ይቅርና ከክርስቲያኖቹ የጦር አለቆችም ውስጥ ተስፋ እየቆረጡ የሚገቡት ለመግባት የሚላላኩት ብዙ ስለሆኑ በርሱ ሊፈረድበት አይችልም ። በአሁኑ የግ ራኝ ሥልጣን በሸዋና በደቡብ አገሮች በሰፈነበት ሰዓት ሁሉም ግራ ሳይገባው አይቀርም ። ሁኔታው በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በማይጨው መልስ ከነበረው አኳኋን ጋር ተመሳሳይ ነው ። ከማይጨው መልስ ግማሹ ወደ ስደት ግማሹ ወደ አርበኝነት የቀ ረውም ወደ ኢጣልያ መግባት እንዳመራ በዚህም ግራኝ ባሸነፈበት ሰዓት ያለው መንገድ ሦስት ብቻ ነው ። ፩ኛው ጓዝን ጠቅልሎ ንጉሡ ወደሄዱበት ወደሰሜን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 213 - 255

አቃንቶ መሸሽ ፤ ፪ኛው ለግራኝ ገብቶ ሰልሞ እየገበሩ መኖር ፤ ፫ኛው ሸሽቱንም መሰለሙንም የጠላው ከግራኝ ጦር ጋር በአርበኝነት እየተዋጉ ለሀገርና ለሃይማኖት መሠዋት ነው ። የጦር አለቆቹ እንደ ስሜታቸው ከሦስት እንዳቸውን መስመር መከተል ግዴታቸው ስለሆነ የአውራይ ኡስማን ምርጫ ያለፈው በዚሁ በ፪ኛው ቁጥር ባለው ላይ ነው ማለት ነው ።

አውራይ ኡስማን ወደ ግራኝ ሲገባ አምኖ የተከተለውን የክርስቲያን ጦር በክዳቱ አሳምኖ አብሮ ይዞ ለመግባት ፤ እንደ ልጅ የሚመለከተውን አናንያን ወደሱ አሳብ ለመምራት በጉዳዩ ሲጨነቅበት ሰንብቶ ሁለቱም በመጨረሻው ተስማምተው የተከተላቸውን ጦር ይዘው ለግራኝ ገቡ ። ግራኝም በጣም ተደስቶ ከገቡ በኋላ ኡስማንና አናንያን የቀድሞ ጌታቸውን ንጉሡን እያባረሩ ከግራኝ ጦር ጋር በማበር ይወጉ ዠመር ። በተለይም ከመሠረቱ እስላም የነበረው ከአውራይ ኡስማን የበለጠ ክርስቲያን የነበረው አናንያ ከሰለመ በኋላ መንገድ በመምራት የሚያውቀውን መላና ምሥጢር በማገለጥ የራሱንና የወገኑን አገር በሹመት ያስቀመጡትን ንጉሥ ዞሮ በመውጋት በድሏል ። አሁን ሁለቱም ወደ ግራኝ የገቡበትን ሁኔታ ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

«የይፋትን ግዛት ላንተ ነውና የምሰጥህ ሂድና አገሪቱን ያዝ ብሎ ይማም ለባሕር ጦር መሪ ለሻምሱ ነገረው ። ሻምሱም ወደ ይፋት ሄደ ። አገሩ ለፈረስ አይመችም ነበርና በእግር ሄዶ ከአገሬው ሕዝብ ጋር ተዋጋ ። ሕዝቡም በተራራ ላይ ሆኖ እንደተከበበ ሲዋጋ ቆይቶ መጨረሻውን ተሸንፈና ሁሉም እየገባ ሰለመ ። በዚያም አንድ የቀድሞው ንጉሥ ዓፄ እስክንድር ያሠራት ቤተ ክርስቲያን ነበረች በውስጧ ብዙ ወርቅ ነበር ። ንጉሡ ነዋየ ቅድሳቱን በወርቅና በብር አሠርቶት ነበር ። በዚያም አንድ በወርቅ ሥራ የተጠረዘ . . . . . . ትልቅ ወንጌል ነበር ። እርሱንም ከመሬት ለማንሣት ሁለት ጠንካራ ሰው ያስፈልግ ነበር ። ሻምሱ ወደ ውስጧ ገብቶ በውስጧ የሚገኘውን ሁሉ የ፶ ወቄት ወርቅ ጌጥ ያለበት ያዓፄ እስክንድርን በርኖስ (ካባ) ጭምር ወስዶ ከጨረሰ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑን አቃጥሎ ወደ ይማም ተመለሰና ያገኘውን ሁሉ አስረከበው ። ይማምና ጓደኞቹም የወርቁን ወንጌልና ሥዕሉን እያዩ አደነቁ . . . . . ። ከዚያ ደግሞ እኔ እከተልሃለሁና እፊት ቀድመህ የይፋትን ሕዝብ እየወጋህ እሳምን ብሎ ገራድ እህሙሽን ላከው... ከሐዲው አውራይ ኡስማን ወሰን ሰገድ የሞተ ጊዜ ወደዚህ ወደግዛቱ ወደ ይፋት መጥቶ ተቀምጦ የጋፋትን የወናግ ጃራን ጦር ሰብስቦ ይዞ ነበር ። ይማም አቡናህ የገባ ጊዜ እስላሞቹን እወጋለሁ እንጂ በአገሬ (በይፋት) አላስገባቸውም ብሎ ለወታደሮቹ ተናገረ ። ባንድ ወገን ደግሞ ከወታደሮቹ በድብቅ አድርጎ "ጥንትዘሬም እኔም እስላም ነን ። ነገር ግን ከባሌ ክርስቲያኖቹ ወስደው ክርስቲያን አደረጉኝ ። ልቤ ግን ሁልጊዜ ከእስላምነት አልተለየም ። አሁን ግን ወደ አላህና ወደ ነቢዩ ወዳንተም መመለስ ስለምፈልግ ባለፈው ጥፋቴ የማትቀጣኝ እንደሆነ ወዳንተው እገባለሁ እዚህ ከኔ ጋር ያለውንም የንጉሡን ጦር አንድ ተንኮል ሠርቼ ወዳንተ ገብተው እስላም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ብሎ ደብዳቤ ጽፎ በይፋት እስላሞች

እጅ ወደ ይማም ላከ ። ይኸንንም ምሥጢር ለማንም ክርስቲያን እንዳትገልጹ ብሎ አስጠነቀቀ ።

ይማም ከመልክተኞቹ ደብዳቤውን ተቀብሎ ነገሩን ከተረዳ ወዲህ ወሬ አግ ኝቻለሁና ተመለስ ብሎ ወደገራድ አህሙሹ ልኮ መለሰው ። ይማም የአውራይ ኡስማንን ደብዳቤ ከተመለከተ በኋላ ከአመፃቸው ተመልሰው የክህደትን ሥራ ለማይሠሩት ያለፈ ኃጢአታቸውን ይሠርይላቸዋል የሚለውን በቁራን የተጻፈ ውን የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሶ (1) በአለፈው ይቀጣኛል ብለህ አትስጋ አት ፍራ ስለዚህ ጦቢያ ላይ እንገናኝ ብሎ የመተማመኛ ምልክት ላከለት ። ደብዳቤው በምሥጢር ደረሰው ። በዚያን ጊዜ ምን ይሻላል ብቻዬን ነኝ ፣ ብቻዬን ወደ ይማም ብገባ ባለፈው በእስላሞቹ ላይ በሠራሁት ሥራ ያሥፈሩኛል ።እነዚህን ያሉኝን የክር ስቲያን ወታደሮች ከኔ ጋር እስላም ሁኑ ብላቸው ይገድሉኛል ወይም አሥረው ምር ኮኛ ያደርጉኛል እያለ ብቻውን ሲያወጣ ሲያወርድ ቆይቶ ሾክርና ያኪም የሚባሉ ሁለት እስላሞች አፊቱ አስመጣ ። ከነዚህም ከሁለቱ ሾክር በነፍስ ግዳይ ያኪም በዕዳ ምክንያት ከይማም ከድተው ወደ ንጉሡ ገብተው በሹመት በይፋት የሚኖሩ ናቸው ። እነሱንም ይማም ይኸው እቅርባችን ነው ያለው ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ወደ አገራችን ገብቶ ይዘርፈናል ። ስለዚህ ጦራችንን ይዘን ወደ ንጉሡ እንሽሽ ወይስ እዚሁ ተዋግተን እንሙት የትኛው እንደሚሻል እስኪ ምክር አምጡ ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም እኛ አገልጋዮችህ ነን እንሽሽ ወይም እንዋጋ አለዚያም እንስ ለም ብትለን እንደፈቃድህ ከመፈጸም በቀር የምንሰጥህ ምክር የለም ብለው መለሱ ለት ። እሱም እኔ ካነሳሁት ከመዋጋቱም ከመሸሹም የተሻለው ይኸው ወደ ይማም መግባቱና መስለሙ ነው ፣ ስለዚህ ወደርሱ ሂደን ላለፈው ጥፋታችን ይቅርታ እን ዲያደርግልን እንለምነዋለን ። እኔም ደብዳቤ ጽፌለት . . . . . ለኔም ለናንተም የሚ ሆነን የመተማመኛ ምልክት መልስ ልኮልኛል ። ነገር ግን ይህን የያዝነውን የክር ስቲያን ጦር እንንደምን እናደርገዋለን እኛንስ ተከትሎ እንደምን ወደ ይማም ይገ ባል እያለ ጠየቃቸው አንተ ለሕይወታችን ዋስትና ከሰጠኸን ግድ የለም ለዚህ እኛ እንበቃለን አሁንም አገልጋይህን አናንያን ጥራውና ይምጣ አሉት ።

አናንያ ከአውራይ ኡስማን በታች ሆኖ ጦሩን የሚያዝ የክርስቲያን ሹም ነው ። ስለዚህ አናንያ ይኸንን አሳባችንን ቢሰማ የሚቀበለን ይመስላችኋልን ብሎ ቢጠይቃቸው እርሱ እንተ እሳትም ልግባ ብትለው እብሮህ ይገባል አሉትና ከዚያ ወዲያ አናንያ ተፈልጎ መጣና አውራይ እንደዚህ አለው "አንተ ልጄ ምክትሌ ነህ ይኸን ሁሉ የደረሰብንን አይተሃል ምን ማድረግ የሚሻል ይመስልሃል" ብሎ ጠየ ቀው ። በዚያን ጊዜ አናንያ በእጅህ ውስጥ እንዳለሁ ምርኮኛ ወደምትሄድበት እሄዳለሁ ። እንዋጋ ብትለኝም ወደ ንጉሡ ሸሽተን እንሂድ ብትለኝም የምታዘኝን ብቻ አፈጽማለሁ ሲል መለሰለት ። አውራይም በል በፊቱ ከቃሌ ላትወጣ ማልልኝ ቢለው ማለለት ። ከዚያ ወደ ይማም ለመግባትና ወደ እስልምና ለመመለስ ማሰ

(1) በቅርብ ወደ አማርኛ የተተረጐመው ቁራን ምዕራፍ (ሱራት) ፰ ቍጥር ፴፰ - ፴፱

ቡን ገለጸለት ። እርሱም እኔም ከዚህ ቀደም ወደ ማርጃይ አገር ሾመህ የላክኸኝ ጊዜ ወደ ይማም ተላልኬ ለመስለም አስቤ ነበር ። ነገር ግን ሳላደርግ የቀረሁት ላንተ ፍቅር ስል ነው ሲል መለሰ ። በዚያን ጊዜ አውራይ ትልቅ ደስታ ተሰማው ታዲያስ ለጦር ሠራዊቱ እንዴት አድርጎ መንገር ይሻላል ቢለው የዚህን ጉዳይ ለኔ ተወው መጀመሪያ በአንተ ዙሪያ የሚያገለግሉህን እንደ ቤተ ሰብ የሚሆኑትን ነገሩን ገልጬ እነግራቸዋለሁ እሺ ቢሉ መልካም ነው እምቢ ቢሉ እንዋጋቸዋለን ብሎ መለሰና ከዚያ ወጥቶ ለ፶ ፈረሰኞች ለ፪ሺ የእግረኛ ወታደሮች ቢገልጽላቸው እኛ ጌታችን እሳት ቢገባ እንገባለን የኛ ጉዳይ የእርሱን ትእዛዝ መከተል ብቻ ነው እያሉ መለሱለት ይኸንንም ቃል ወስዶ ለአውራይ አስታወቀ . . . . . ወናግ ጀራ የሚያዛቸው ፩ሺ የሚሆኑ የክርስቲያን ጦር ሠራዊት ነጭ ተራራ መስለው ይታዩ ነበር በባሕር አምባ እነሱን የመሰለ ጦር የለም ።

አውራይ ኡስማን ወደ ሜዳ ወርዶ ጦሩን ያሰለፈ ጊዜ የወናግ ጀራ ጦር ወዴት ሄደ ምነው አይታዩኝ ብሎ ቢጠይቅ ከተራራቸው አልወረዱም አሉት ። ወደ ተራራ ቀና ብሎ ቢመለከት ለውጊያ ተሰልፈው አያቸው ፤ ከዚያ ምን ሆናችሁ እኔስ ምን በደልኋችሁና ተለያችሁኝ ብሎ መልክተኛ ቢልክባቸው ያንተን አሳብህንና ንጉ ሡን መክዳትህን አውቀንብሃል እኛ ግን የእርሱ አገልጋዮና በፊቱ የምንሞት ነን ። ስለዚህ ወዳንተ እንመጣም ከኛ ጋር መዋጋት ፈልገህ እንደሆን ወደ ተራራው ብቅ በል የሚል መልስ ላኩለት ። ይህን ከላኩለት በኋላ እነሱ ጋሻቸውን እየራሳቸው ላይ አድርገው ወደ ቤተ አምሐራ (ንጉሡ ወደ ሄዱበት) ጉዟቸውን ያዙ ። አውራይ ኡስማን ያገሩን ሰው እስላሙን ሁሉ በሙሉ ይዞ ወደ ጦቢያ ሄዶ ይማምን ይጠባበቅ ገሠመር ።

ISIC

ይማም በዚህ ጊዜ የመኖሪያ ሥፍራው በአቡናህ ነበረና ከአውራይ ኡስማን ለመገናኘት ወደ ጦቢያ ሄዶ በሩቅ የአውራይን የተተከለ ድንኳን ተመልክቶ በዚያ አቅራቢያ ሠፈረ ። ከዚያ በኋላ አውራይ ኡስማን ያለበትን ሥፍራ ትቶ የፈረሰኛ ወታደሩን አሰልፎ የሚያማልዱትን ሼኾችና ሊቃውንት ከፊቱ አስቀድሞ ወደ ይማም መጣ ። ወደ ድንኳኑም ገብቶ እጁን ሳመው ። ይማም አህመድም በመል ካም ተቀብሎ ወዲያው አትፍራ አለው ። ወደ ወታደሮቹም ዘወር ብሎ እንግዲህ እስላም ሁኑ አላቸው ። በዚህ ምክንያት ከእኩለ ቀን ገምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ወንዱም ሴቱም ሁሉም ሲሰልሙ አመሹ ። ቍጥራቸው እስከ ፳ሺ ይደርሳል ይማም እግዚአብሔርን አመስገነ አውራይንም ባረከው . . . . . ወደ አገራቸው ለመመለስ የሚፈልጉትን ኤሚሮች ሁሉ ይዞ ዝቋላ በተቀመጠው በወዚር አዶሌ ውስጥ እንዲተዳደሩ አደረገና ደብረ ብርሃን ጦር ይዞ ይጠባበቅ ለነበረው ለፈራቃ ሃም አሊ የአውራይን (1) መግባት ከገለጸለት በኋላ በደብረ ብርሃን ሥራ ፈቶ እንዳ ይቀመጥ ወደ ተጉለት ወደ ወግዳ ወደሙገር እየዘመትህ አገሩ ሁሉ እስኪገብር

(1) ለፋራቃሃም አሊ መላኩ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ኡስማን ለፋራቃሃም አሊ አማቹ ስለነበረ ነው ፤

ድረስ ውጋው ብሎ ላከበት ። እርሱም ራሱ ወደ ደብረ ብርሃን ለመሄድ አስቦ ሳለ በአውራይ ኡስማንና በአዝማች ሃይቢ ምክር ወደግድም ሄደ የዚህን አውራጃ ሕዝብ አሰለመ . . . . .» ሲል ጸሐፊው ስለ አውራይ ኡስማን ወደ ግራኝ መግባት ያትታል ።(1) ።

አውራይ ኡስማን በርሱ ደረጃ ያሉት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከግራኝ ጦር ጋር ብዙዎቹ እየተዋጉ ሲያልቁ የተረፉት ከንጉሡ ጋር ወደ ቤተ አምሐራ (የዛሬ ወሎ) ሲያመሩ እርሱ ወደ ይፋት ሄዶ ጦሩን በማግባባት አሳድሞ ወደ ግራኝ የገባበት ዋናው ምክንያት ጊዜ ካነሣው ካዲሱ ባለሥልጣን ጋር ሆኖ በሹመት እየተደሰተ ዕድሜውን ለመቀጠል መሆኑ የታወቀ ነው ። ይኸንንም ለማግኘት ራሱም ወታደሩንም አሳድሞ ለግራኝ መግባቱ ብቻ አልበቃም ። ነገር ግን አዲሱን ጌታ ለማስደሰት ቀድሞ በሹመት አክብሮ ያስቀመጠውን ጌታውን እያባረረ መውጋት አለበት ። በማናቸውም ቢሆን በተለይ በግራኝ ዘንድ በግማሽ መታመን በግማሽ መክዳት አይፈቀድም ። ስለዚህ አውራይ ኡስማን ዓፄ ልብነ ድንግልን እስከተቻለው አገልግሎ አሁን በሙሉ ሲከዳ ለግራኝም በሙሉ ሥልጣን በሙሉ ፈቃድ በሙሉ ታማኝነት አገልግሎቱን መግለጽ አለበት ። በዚያ የሰው ልጅ ነፃነት በሌለበት ሰዓት እላይ እንዳልነው የቀዘቀዘ መካከለኛ ኑሮ ማግኘቱ ችግር ነው ። ስለዚህ አውራይ ኡስማን የከረምቱን ወራት ሐምሌንና ነሐሴን ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በዝሆን ዱር (ዳሞት) በወጅ ከንጉሠ ነገሥቱና ከራስ ወሰን ሰ፲፫ ጋር ከቆየ በኋላ በነሐሴ ፳ ቀን ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ወሰን ሰገድ ስለሞተ በነሐሴ ወር መጨረሻ ወይም በመስከረም መዠመሪያ ላይ ለግራኝ ገብቶ የቀድሞ ሃይማኖቱን አቀፈ ።

በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. በጥቅምት ወር ከግራኝ ጋር ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ ከንጉሡ ጦር ጋር መዋጋቱን ቀድሞ አምባ ግሼንን ለመያዝ ከነቢትወደድ ሠርፄ ጋር በኅዳር ወር ሲዋጋ በቀድሞ ጓደኞቹና በከዳቸው በክርስቲያኖቹ እጅ ተመትቶ መሞቱን ወደፊት እናነባለን ። እንግዲህ ዓፄ ልብነ ድንግልን ከከዳበት ጊዜ ገምሮ እስኪሞት ድረስ ያገኘው ሕይወት ቢበዛ የአራት ወር ዕድሜ ነው ። ይኸን በቅድሚያ የማወቅ ችሎታ ቢኖረው ኖሮ ታላላቅ አውራጃ አንድ ጊዜ ፊጠጋርን አሁን ይፋትን እየሾመ ያንቀባረረውን ጌታ ባልከዳም ነበር ።

ምናልባት ከዓፄ ልብነ ድንግል ሳይለይ ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ ቢሆን ኖሮ የበለጠ ዕድሜ ባገኝ ነበር ። በሚያየው የጦርነት አያያዝ ንጉሡ ተሸናፊ ግራኝ አሸናፊነቱን በትክክል ሲመለከት የርሱን ባጭር ጊዜ መሞት በፍጹም ሊመለከተው አይችልም ። ይህ ከብልሆች የሚደብቀው የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ችሎታ ብቻ ነው ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 272 - 281

## ምዕራፍ ፶፮
## በሸዋ ከተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ (፲፭፻፳፫ - ፳፬ ዓ. ም.)

ከራስ ወሰን ሰገድ ሞትና ከአውራይ ኡስማን ወደግራኝ መግባት በኋላ ከቀድሞው የበለጠ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸው የታወቀ ሲሆን ትክክለኛ ቦታቸውንና ስማቸውን የዓረቡ ጸሐፊ መግለጽ እያቃተው በደፈናው የባደቂ ቤተ ክርስቲያን ወይም ዓፄ ናዖድ ያሠራት ዓፄ እስክንድር ወይም ራስ ወሰን ሰገድ የተከላት ከማለት በቀር ትክክለኛ ቦታውንና የቤተ ክርስቲያኑን ስም ስለአልጠቀሰው የአብዛኛው አልታወቀም ። በኛም በኩል ዋናው ታሪክ ነገሥት በቤተ አምሐራ ያሉትን ወደፊት እንደምናነበው ሲዘረዝር በደዋሮ በፈጠጋር በመራቤቴ ፤ በይፋትና በመንዝ በግድም በባሌ ፤ በጉራጌ ፤ በሐድያ በጠቅላላው በሸዋ የተደረገውን የጦርነት ታሪክ ከመተረክ እንደተቆጠበው ሁሉ የተቃጠሉትንም የአብያተ ክርስቲያን ስምና ሥፍራ እየለየ አልዘረዘረም ።

ይሁን እንጂ ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ በዚህ ክፍል ያለው መላው የዛሬ የከረዩና የአካባቢው ያን ጊዜ ደዋሮ የሚባለው እንደዚሁም የባሌና የአሩሲ ፤ የሐረርና የሸዋ ጠቅላይ ግዛት በእጁ ስለወደቀ በደብረ ሊባኖስ ቃጠሎ ላይ እንዳነበብነው «ዝረፍ አቃጥል ግደል» በሚል በጠቅላላ ዓላማ ግራኝና ሹማምንቱ በያለበት እየተሰራጩ በፊታቸው የወደቀውን ቤተ መንግሥት ፤ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ወይም በየዕቃ ቤቱ የታጀለውን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ዕቃ ፊት ለፊት ያገኙትን በጠቋሚ የደረሱበትን ሁሉ ሙልጭ አድርገው ከዘረፉ በኋላ እሳት እየለኰሱ ማጋየት ሕዝቡን ማስለም እምቢ ብሎ ለመመከት የሞከረውን መፍጀት ዋና መሠረታዊ አሳባቸው ስለሆነ ይኸንኑ ባዲስ ኃይልና በቀል ፈጽመዋል ። በዚህም ላይ በአሁኑ ጊዜ የግራኝ ፍላጐት ንጉሡን ለመማረክ ወይም ለመግደል እርሳቸውም ሲሞቱ መላው አገር ይገዛል በሚሉ ምኞት እርሳቸው ወደሄዱበት ወደ ቤተ አምሐራ ለመዝመት ስለሆነ የዛሬውን የከፋን ፣ የሲዳሞን ፣ የወለጋን ግዛት ለጊዜው ችላ ብሎታል ።

ከዚህ በፊት ያቃጠለው የቤተ መቅደስ ስሙና ያለበት ቦታ ሁሉ የአንዳንዶቹ በትክክል ባይታወቅም የተቃጠሉትን በየምዕራፉ አንብበናል ። አሁን ደግሞ አንድ ባማርኛ የተጻፈ ደራሲውን የማይጠቅስ ጽሑፍ በተጉለት የደብረ ብርሃን በመንዝ የምስሐለ ማርያም አብያተ ክርስቲያን መቃጠላቸውን ለይቶ ይጠቅስና በየካቲት ፲፬ ቀን በደፈናው ከዋያት ወንዝ በመለስ ያለው መቅደስ ሁሉ መቃጠሉን ያመለክታል ። በዛሬው አዲስ ዓለም አቅራቢያ ያን ጊዜ እንደገብጣን በሚባለው ወረዳ የቅዱስ ፊቅጦር ፤ በዛሬው አዲስ አበባ አካባቢ ያን ጊዜ እንዶጥና በሚባለው ሌላ ገዳም እንደዚሁም በይፋት አቅራቢያ ደብረ ምሥዋዕ የሚባል ገዳም መኖሩ በሌላ ጽሑፍ ላይ ተጠቅሶ ስለሚገኝ እነዚህ ሁሉ ባሁኑ ጊዜ የእሳት ራት ከመሆን አልዘለሉም ።

ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በፈጠጋር ጥልቅ በምትባለው በተወለዱባት ቦታ ሁለት

አብያተ ክርስቲያናት አሠርተው አንዱን መርጡለ ሚካኤል ሁለተኛውን ዓጸደ ሚካኤል ብለው ሰይመው ከዚያ ደግሞ ወደ እንዘርጻ (?) ወረዳ አልፈው ደብረ ስሂን የሚባለውን መትከላቸውን ቀጥሎ በግብፅ አገር ደብረ ምጥማቅ የምትባለ ዋን ገዳም እስላሞች (ግብጾች) አቃጠሏት ማለትን ሰምተው ግዴለም እዚያ ቢያቃ ጥሏት እኛ እዚህ በአገራችን እንሠራላታለን ብለው በተጉለት አዲስ ቤተ ክርስቲ ያን አሠርተው ስሟን ደብረ ምጥማቅ እንዳሰኙዋት ከዚሁ አያይዞ በተጉለት ለእ መቤታችን ምስልና ለመስቀል መስገድ አይገባም ብለው የተነሡት የእስጢፋኖስ ልጆች . . . . . . በተቀጡ ጊዜ (1) በተጉለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ለብሶ ስለታየ ወይም ብርሃን ስለወረደ በዚያ በስሙ ያሠሩትን ቤተ ክርስቲያን ደብረ ብር ሃን ብለው እንደሠየሙት በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ በምድረ ደጎ መካነ ማርያምን በቤተ አምሐራ ደብረ ነጐድጓድን እንዳሠሩ ዜና መዋዕላቸው በየምዕራፉ ያመለክ ታል ። (2) ።

በበኩላቸው ያፄ ዘርዓ ያዕቆብ ልጅ ዓፄ በዕደ ማርያም ቤተ አምሐራ ሄደው አትሮንሰ ማርያምን ተክለው ከተመለሱ በኋላ በመንዝ በኩል ሲያልፉ ለቤተ ክርስ ቲያን ሥራ ተስማሚ የሆነ ቦታ ፈልገው ያማረ ቤተ ክርስቲያን ካሠሩና ከአስጨ ረሱ በኋላ ከመራቤቴ (መርሐ ቤቴ) ብዙ ታቦታት አስመጥተው እንዳስገቡበትና የቤተ ክርስቲያኑን ስም ምስሐለ ማርያም ብለው በእመቤታችን ስም እንደሠየ ሟት ዜና መዋዕላቸው ይገልጻል (3) ። ምስሐለ ማርያም ያለውን በሌላ ቦታ "ሥሕል ቤት" ሲለው ይገኛል ወደ ዘመናችን ቀረብ ያለ አንዳንድ ጽሑፍ ምስዓለ ማርያም ይልና ሥዕል ቤት ያደርገዋል ። በሕዝብ አነጋገር ደግሞ ምስዋለ ወይም ምስለማር ያም ይባላል ።

እስከ ዛሬ ድረስ ነገሥታት በሌላው በየአውራጃው ከመትከላቸው በቀር በሚ ኖሩበት ቤተ መንግሥት አጠገብ ጪት ማታ የሚጸልዩበት ቤተ ክርስቲያን ያሠ ራሉ ። በዚያም ብዙ ታቦታት ያስቀምጣሉ ። እነዚህንም በዘመቻ ጊዜ ለተራዳኢ ነት (እንዲረዱዋቸው) ይዘዋቸው ወደ ጦርነት ይዘምታሉ ። ያፄ ምኒልክ ስዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ከታላቁ ግቢ እንደነበረ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እላይኛው ግቢ የነ በሩ ጊዜ ማርቆስ አሁን ደግሞ ለኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥታቸው በቅርብ ያለው እስጢፋኖስ ወይም በግቢያቸው ውስጥ ያለው ቤተ ክርስቲያን የስዕል ቤታቸው ነው ማለት ነው ። ይኸም ሁሉ ከዚያው ከጥንቱ ተያይዞ በመጣው ልማድ ነው ።

(1) ደቀ እስጢፋኖስ (የእስጢፋኖስ ልጆች) በሐይቅ በእስጢፋኖስ ገዳም የሚኖሩ ካህናት ናቸው ።

(2) ያፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ዢል ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 51 - 55 - 67 - 68

(3) ወእምሕየ ተመይጠ አትሮንሰ ማርያም ወእምድኅረዝ ተንሥአ ንጉሥነ ውእቱ (በእደ ማርያም) ውንለፈ ምንዝህ (መንዝህ - መንዝ) እንዘ የሐሥሥ ሠናየ መካነ ከመ ካዕበ ይሕንፅ መቅደሰ ፈቀዶ ወረከበ ሶቤሃ ዘከመ ሐለየ መካነ ኅሩየ ወተፈሥሐ ፈድፋደ ወወጠነ ሱራሬሃ ወገብረ ሰቀላ ወአውጽአ ብዙኃ ታቦታተ እመርሐ ቤቴ ወአብአ ውስቴታ ወሠመያ ምሥሐለ ማርያም ። ያፄ ዘርዓ ያዕቆብና ያፄ በእደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ 126 - 128 ።

እንግዲህ ከይኩኖ አምላክ ዠምሮ እስከዚህ እስከ ግራኝ አህመድ ወረራ ድረስ ያሉት ነገሥታት ቍጥራቸው ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ፳፬ ፣ ዘመኑ ከ፲፭፻ ፷፪ ዓ. ም. ጀምሮ ዓፄ ልብነ ድንግል እስከ ነገሡበት እስከ ፲፰፻ ዓ. ም. ድረስ ሁለት መቶ ሠላሣ ስምንት ዓመት ስለሚሆን የነገሡበት ጊዜ በማጠሩ ወይም ሞት እየቀደማቸው ካልቻሉት በቀር አብዛኞቹ ነገሥታት ብዙ ሀብት እያፈሰሱ በዚሁ ለምሳሌ ያህል በተመለከትነው ባዔ ዘርዓ ያዕቆብና ባዔ በዕደ ማርያም ዓይነት በያ ለበት ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን የገደሙት ገዳም የከተሙት ከተማ ብዙ ነው ። በዚ ህም ስማቸው የተጠራ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ዓፄ ሠይፈ አርእድ ዓፄ ዳዊት ዓፄ ይስ ሐቅ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ዓፄ በዕደ ማርያም ፣ ዓፄ እስክንድር ፣ ዓፄ ናዖድና ልጃ ቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ናቸው ። የዚያን ጊዜ የተቃጠለውን የቤተ ክርስቲያን ብዛት ለመረዳት በየአውራጃው እየተዘዋወሩ ያሁኖቹን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት መመልከት ይበቃል ። ከዚያ ወዲህ ከተጨመሩት በቀር አብዛኞቹ የክርስ ቲያኑ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ በየነበሩበት ቦታ ተመልሰው የተሠሩ ናቸው ።

እነዚህ ሁሉ በአሁኑ ሰዓት የእሳት ራት ሲሆኑ በውስጣቸው የተገኘው የደለበ የልብስና የወርቅ ሀብት ከመዛሪያ መግዣ የተረፈው የእስላሞቹን ኪስ አትረፍ ርፎ ሞልቶታል ። የቃጠሎውና የዘረፋው ሁኔታ በዚያው የዘመቻውና የወረራው በተተረከበት በየምዕራፉ ላይ ይገኛል ።

ISIC

## ምዕራፍ ፶፯

## በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የኑሮ ዕድል በየጊዜው መለዋወጥ ።

ባለፈው ዘመን በሸዋ ከነበሩት ነገሥታት ከወደ ይፋት ከአዳልና ከአካባቢው ገራድ እገሌ ሸፈተ ከተማና መንደር ዘርፎ አቃጠለ ፣ የይፋት ወላስማ የተለመደ ውን ግብር ከልክሎ አስገባሪውን ሹም አሥሮ አጉላላ ከንጉሡ ነገሥቱ ሸቀጥ ለማ ምጣት ወደ ዓረብ አገር የሚሄደውን ወይም ደርሶ የሚመለሰውን የያዘውን ሸቀጥ ቀምቶ አሠረው በተባለ ቍጥር ተቀማጭነታቸው ተጉለት (ደብረ ብርሃን) መንዝ ወይም የረር የሆነው ነገሥታት ነገሩ ከበድ ሲል ራሳቸው በመዝመት ቀለል ሲል የጦር መኰንን በመላክ የሸፈተውን ሲያባርሩ ሲይዙ ፣ ሲያስሩ ፣ ሲፈቱ ፣ ከተማውን ፣ መንደሩን ፣ መስጊዱን ሲያፈራርሱ ፣ ሲያቃጥሉ መኖራቸው የታወቀ ነው (1) ።

ሠይፈ አርእድ ዓምደ ጽዮን ዘርዓ ያዕቆብ የቀሩትም በዚህ በኩል ተላልፈው የመንግሥት ሥልጣን ባዔ ልብነ ድንግል እጅ ከሆነበት ከ፲፮ኛው ዓመት ዠምሮ ሁኔታው ተገላብጦ እነሆ ግራኝ አህመድ ከሐረር እየተመላለሰ በመዋጋት ንጉሡ

(1) የዓምደ ጽዮንን የጦርነት ታሪክና ያፄ ዘርዓ ያዕቆብን ዜና መዋዕል በየምፍራው መመልከት ይበ ቃል ።

ነገሥቱን ከነሠራዊታቸው በየጦሩ ግንባር አሸንፎ ወደ ቤተ አምሐራ በተለይ ዛሬ ወረይሉ ያን ጊዜ ዋስል ወይም እንደ ግዕዙ ሐን እንደ አማርኛ አቋ ወደሚባ ለው አገር እንዲሸሽ አደረጋቸው ።

ነገሥታቱ ወይም የጦር አለቆቻቸው ባለፈው ዘመን በእስላሞቹ ዜጎቻቸው ላይ ከፈጸሙት የዘረፋና የቃጠሎ ጥፋት አሁን ግራኝ አህመድ በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ የፈጸመው እንደሚበልጥ የምንረዳው ባለፈው ካደረገው በቀር ወደፊት በቤተ አምሐራ በላስታ ፥ በትግሬ ፥ በጸለምት ፥ በጸገዴ ፥ በቤገምድር ፥ በጐጃም የሚያደር ገውን ስንመለከት ነው ። ይኸን የመሰለው የአጥቂነትና የተጠቂነት የመሸነፍና የማሸነፍ ዙር የገዥነትና የተገዥነት ዕጣ ፈንታ በዓለም ካገር ወደ አገር ፥ ከነገድ ወደ ነገድ እየተዘዋወረ እንደኖረ ይኸው ነዋሪ ሕግ በኢትዮጵያ ገዥዎችና ተገዥ ዎች ላይ መፈጸሙ ነው ። በአክሱሞች ጊዜ የደረሰው የፈላሾችና የአገዎች አጥቂነ ትና የአክሱሞች ተጠቂነት ከዚሁ ዕድል ጋር የተያያዘ ነው ። ወደኋላ ራቅ ብለን በዓይኑ ሕሊናችን ታሪክ ብንመለከት የአውሮፓ የነጭ ዘር ቆዳ ለባሽ በጫካና በጐሬ ወይም በደሳሳ ቤት ነዋሪ ፥ ፊደልና የሥነ ጽሑፍ ሞያ የሌለው ፥ የሕንፃን የስዕልን ጥበብ የማያውቅ ፥ እንደ አውሬ መንጋ እየተግበሰበሰ በሚኖርበት ጊዜ የግብፅ ፥ የከለዳውያን ፥ የአሶራውያን ፥ የፋርስ ፥ የሕንድና የቻይና ሕዝቦችና ገዥ ዎች ከክርስትና በፊት በነበረው የሺና የሁለት ሺ ዓመት ዘመን ውስጥ በሕንፃ የሚኖሩ በብርና ባጌጠ መሣሪያ የሚጠቀሙ[illegible]ሐር ልብስ የሚሽሞነሞኑ በሥነ ጽሑፍ በፍልስፍና የሚራቀቁ እንደነበሩ እንረዳለን ፥ ሁለቱም ወገኖች በዚህ አቅ ዋም እስከ መጨረሻ ሊዘልቁ አልቻሉም ።

ክርስቶስ ሊወለድ አቅራቢያ በነበረው ፭፻ ዓመት ከተወለደ በኋላ ባለው የሺ ዓመት ዘመን ውስጥ ሁኔታቸው የገላቢጦሽ ሆነ ። ሥልጡኖቹ ሁሉ ወደቁ ፥ የእጅ ጥበብ ሥራቸው የአእምሮ ርቀታቸው የዕውቀት ቅርሳቸው አንድ ባንድ ወደቀ ተወላጆቹ በዘመን ብዛት የገዛ ዕውቀታቸውንና ሥልጣኔያቸውን ረሱት ።

በግሪክ ቀደምትነት በሮማውያን ተከታይነት በፊተኛው ዘመን እንደ አውሬ ይኖሩ ነበር የተባሉት የአንግሎ ሳክሶንና የላቲን ተናጋሪ ዘሮች በየዕውቀቱ ስልት ከቀድሞዎቹ የበለጡ ሥልጡን ኃያል ሆነው የነዚያን አገር እስከ መውረር ደረሱ ። እነዚያን የቀድሞ ሥልጡኖች ዝርያዎች እንደበቱ እንደ አልፈታና እንደሚድህ ልጅ አድርገው የራሳቸውን አዲስ ጥበብ ከማስተማራቸው በላይ የሞተውንና የተ ቀበረውን የነዚያን የሥልጣኔ ቅርስ ሕንፃውን ሐውልቱን በፍለጋ እያገኙ በላዩ ላይ ያለውን የሂሮግሊፉን የኩኔይፎርሙን የአራማይኩን ፥ የሲሪያኩን ፥ የሳባውን ቋንቋና ፍቺ በምርምር እያገኙ ለራሳቸው ከአወቁት በኋላ ለተገዥዎቻቸውም «ያውላችሁ ዕውቀታችሁ» እያሉ እያስተማሩ ለሞተው ሥልጣኔ አዲስ የትንሣኤ ሕይወት ሰጡት ። ግብጻዊና ከላዳዊ የራሱን ፊደልና ዕውቀት መልሶ የገላቢጦሽ ከገዥዎቹ ፈረንጆች ይማር ገባ ። በዚሁ መሠረት ዛሬም እኛ ኢትዮጵያውያኑ የራሳችንን ለአክሱም ታሪካችን መሠረት የሆነውን የሳባውን የግሪኩን የግዕዙን ነባርና መሠረታዊ የታሪክ ጽሑፍ በአባቶቻችን ዘንድ የተዘነጋውን ከነሊትማን

ከነኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍ መማር ውጤትም ግዴታም ሆኗል ።

በአሁን ጊዜ ደግሞ የምንመለከተው ፈረንጆች ምሥራቅን በተለይ ከሁሉ የባሰ ከ፲፭ኛው መቶ ዓ. ም. ጀምሮ አፍሪካን በስፋቱም በወርዱም ተቀራምተው በመከፋፈል ሕዝቡን ሲገዙት ፤ ሲሸጡት በሀብት የሚከብሩበትን የወርቅና የአልማዝ የብረት ማዕድንና የአትክልት ሥራ የለት ጉርስ ጥራጥሬ ብቻ እየሰጡ በማሠራት ሲያጉላሉት እንደ እንስሳ ቆጥረው ሲንቁት የነበረው ጥቁር ሕዝብ እንደገና አዲስ የአስተዳደርና የሥልጣኔ መንፈስ ባለም ላይ ተፈጥሮ የማኅበራዊና የቁጠባን ገንዘብ በጋርዮሽ አያያዝ የመሠረቱ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች የሚሠነዝሩት ክስና ውቅስ ተጨምሮ ከታላላቅ የዓለም ጦርነቶች በኋላ ስለሕዝብና ስለአገሮች ደህንነትና ሰላም የተቋቋመው የዓለም ማኅበር የደነገገው የነፃነትና የእኩልነት መብት ተጫጭኖ በዚያውም ሰበብ የውስጥ ንቅናቄም ከተፈጠረ በኋላ ተገዥው ጠያይሙና የቀይ ዳማው የመካከለኛው ምሥራቅ አገር ብቻ ሳይሆን እነዚያ በመናቅና በጽኑ አገዛዝ ተይዘው የነበሩት ጥቋቁር የአፍሪካ አገሮች ሁሉ ከ፲፱፻፷ ዓ. ም. ወዲህ አንድ ባንድ ነፃነታቸውን እያቆሙ ከገዥዎቻቸው ጋር በእኩልነት እግር ቆመው በመብት ሊተካከሉ ቻሉ ።

ባንድ የጥቁር መሪ ፊት የቀድሞ ገዥዎች የነበሩት ነጮች ሁሉ አጐንብሰው እጅ የሚነሡበት የጥቁሩ መሪ ተጋብዞ አገራቸውን በሚጐበኝበት ጊዜ በአክብሮት በሆታና በጭብጨባ መቀበል ውዴታም ግዴታም ሆነ ። ዘመን ካመጣው ጋር መተባበርና ጊዜ ለፈጠረው ከመገዛት በቀር ሌላ መውጫ አልተገኘም ። ለጊዜው ከገንዘብና ከሀብት ከሥነ ጽሑፍና ከዕውቀት ተገዥነትና ሞግዚትነት በፍጹም ነፃ የመውጣቱና ከቀድሞዎቹ ጌቶች ካሁን ጓደኞች ጋር በደንብ በሀብትና በዕውቀት የመተካከሉ ጉዳይ ሌላ ጊዜ ቢወስድም ይኸው የተገኘው የእኩልነት መብት ራሱ ለጥቁር ሕዝብ እንደ አንድ ታላቅ ተአምር የሚቆጠር ከሰማይ የወረደ የነፃነት መና ነው ።

በዚህ በ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ባዔ ልብነ ድንግልና በግራኝ አህመድ የደረሰው ሁኔታ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ። እኝህ ንጉሠ ነገሥት አዳልንና ሱማሌን በሸፈቱ ቍጥር እየመቱ እያስገበሩ ከኖሩት አባቶቻቸው ከነዘርዓ ያዕቆብ ከነናዖድ ዙፋንን ከወረሱ ወዲህ እርሳቸው በፋንታቸው በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. የአዳሉን ኤሚር ማኅፉዝን ዋናውን የሐረሩን ሱልጣን መሐመድን በውጊያ አሸንፈው በደስታ ወደ መናገሻ ከተማቸው ተመለሱ ። በ፲፭፻፲፫ - ፳ ዓ.ም. በፖርቱጋሎቹ ጉብኝት ጊዜ የነበረውን የክብራቸውንና የስሜታቸውን ሁኔታ ከአልቫሬዝ መጽሐፍ ተገንዝበናል ። ከ፲፭፻፳ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ግራኝ መነሣት (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) ድረስ ይነስ ይብዛ አሥር ዓመት ያህል በደስታና በዕረፍት ኖረዋል ።

ለፖርቱጋል ነገሥታት ለአማኑኤልና ለልጁ ለሳልሳዊ ዮሐንስ በጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ላይ « . . . . . በኔ ዘመነ መንግሥት የእረፍትና የሰላም ጊዜ ሆኖአል ። በአገሬ ድንበር የሚያጋጥሙኝ እስላሞች ከቶ ቀና ብለው ሊያዩኝ አይደፍሩም ። ፊታቸውን ከቶ ወደኔ አይመልሱም ። የጦር ሹማምንቶቼ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ድል

ይነሣሉ እኔም እንደዚሁ ድል እነሣለሁ . . . . . . እንደ ባሕር አሸዋ እንደሰማይ ከዋክብት የበዛ ሠራዊት ወርቅና ስንቅ አለኝ . . . . . » ያሉትን እናስታውሳለን ። ይኸውም በዚያን ጊዜ የሆነና ከእውነት ያልራቀ አጻጻፍ መሆኑ የታወቀ ነው ።

በዚህ ጊዜ ከቅርቡ ከግዛታቸውና ከአካባቢው ግራኝ አህመድ የአዳልንና የሱማሌን ሕዝብ አስተባብሮ የውጭ እርዳታ ጨምሮ ፊት ለፊት ገጥሞ በጦርነት ያሸንፈኛል ከሸዋ አስወጥቶ እስከ ቤተ አምሐራ ድረስ እያባረረ ቤተ መንግሥቴንና ቤተ መቅደሴን ሁሉ ዘራርፎ ያቃጥለዋል ብለው በፍጹም አልገመቱም ። የርሳቸው ምኞት በዚህ ጊዜ የራሳቸውን የጦር ኃይል ከፖርቱጋል ኃይል ጋር አስተባብረው ቅዱሱን ቦታ ኢየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ቀይ ባሕርን ተሻግረው መካ መዲናን ለማፈራረስ እንደነበር ከደብዳቤዎቻቸው ላይ ያነበብነው ትዝ ይለናል ። የአዳሎቹና የሱማሌዎቹ በግብፆችና በዓረቦች መደገፍ ያሳሰባቸው አለመሠልጠናቸውንም ተረድተውት አሰልጣኝና ጥበበኞች ከፖርቱጋል ንጉሥ መጠየቃቸው ባይቀርም ይህ አሁን በዚህ ከ፲፭፻፳፩ - ፳፬ ዓ. ም. በሽምብራ ኩሬ በአይፈርስ በዝሆንዱር የደረሰው የመሸነፍ ውርደት የስደትና የእልቂት መከራ ይደርስብኛል ብለው አልጠረጠሩም ። ዳሩ ግን እነሆ ባሁን ሰዓት ካገር አገር የሚያባርሩዋቸው ቤተ መንግሥታቸውንና ቤተ መቅደሳቸውን በያለበት የሚያጋዩት የጦር አለቆቻቸውን በየጦሩ ግንባር የፈጁት እነዚያ በፊተኛው ጊዜ «ቀና ብለው አይመለከቱኝም» ያሉ

ISIC

ዋቸው ናቸው ።

ባለፈው እንደተመለከተው በነበራቸው አሥር ዓመት የሰላም ጊዜ ውስጥ በተመኳንንቶቻቸው ምናልባት አብዛኞቹ በግዛታቸው ያለውን ሕዝብ እያስገበሩ በተድላና በደስታ ተውጠው በመለሳለስና በመወፈር የጦር ልምምድን የመውጣት የመውረድን ነገር ፈጽመው ባይረሱትም ዘንግተውት የነበረ ይመስላል ። በዚህ ምክንያት ባለፉት ሁሉ የጦርነት ምዕራፎች ስናነብ አንድ የክርስቲያን የጦር መኰንን ካንድ የግራኝ የጦር መኰንን በእግር ወይም በፈረስ ላይ እንዳሉ ብቻ ለብቻ ተጋጥመው በጦርና በሰይፍ በተደባደቡ ቁጥር አብዛኛውን ጊዜ መትቶ በመጣልና በመግደል አሸናፊው እስላሙ ተሸናፊው ክርስቲያኑ ነው ። ለዚህ ሁሉ ጦርነት ምንጭ የሆነውን የተረከው ዓረብ ፋቂህ ለወገኖቹ በአጻጻፉ በማድላት ዋሽቶ ነው እንዳይባል በጠቅላላው በየጦሩ ግንባር ክርስቲያኖቹ መሸነፋቸውን የራሳችን ጽሑፍ ታሪከ ነገሥቱ አረጋግጧል ። የዓረቡ አተራረኩን ቢያሳጥርም ጸሐፊ ባይሆን የቁራን ጥቅስ ከመጥቀስ ጋር ቃለ አጋኖ ያክላል እንጂ በመሠረታዊ ታሪክ የሚዋሽ ስላልሆነ በረዥሙ የሚተርከው ባጭር ከተመለከተው ታሪከ ነገሥት ጋር ይገጥማል ።

በአተራረኩ ውሸት መጨመር ቢፈልግ ኑሮ ወደፊት በሚደረገው በአምባ ግኼን ጦርነት የወገኖቹን የገራድ ማታንንና የአውራይ ኡስማንን በውጊያ ተሸንፈው መሞታቸውን የዋናውን አዝማች የገራድ አህሙሽን ተማርኮ መገደል መደበቅ ወይም ሳይተርክ ለመዝለል በቻለ ነበር ።

በዚህም ላይ በዚህ ዘመን አስተዳዳሪዎቹ በአስተዳደር በሕዝብ ላይ ግፍ

ይሠሩ እንደነበሩ ፍርዱም በትንሽና በትልቅ ሰው መካከል ያለው የተዛባና አድ ልዎ የከበበው እንደነበረ በየመጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ ይታያል ። የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ በዚያን ዘመን አጠራር የታናናሽ ብላቴን ጌታ የሚባለው አብዲ ናጎ በመሬት የተነሣ ከሊቀ ካህኑ ከፀጋ ዘአብ ጋራ በተጣላ ጊዜ ጉዳዩን መርምረው ፍርድ እንዲሰጡ ከንጉሡ የታዘዙት ዳኞች ለአብዲናጎ በማድላት «ጸጋ ዘአብ የሚ ከራከርበት ምድር ትንሽ ስለሆነ አብዲናጎ ከሚገዛው ምድር ጋር መደረብ አለ በት . . . . . አብዲናጎ ትልቅ ሰው በመሆኑ ገቢው (ከመሬቱ የሚገኘው ግብር) ሊነሣው አይገባም» ብለው እንደፈረዱ በአልቫሬዝ መጽሐፍ ላይ ይገኛል (1) ። በዚህ ላይ የአብዲናጎ ታላቅነት የጸጋ ዘአብ ዝቅተኛነት የፍርዱን ሚዛን ተጭኖ ወደ አድልዎ እንዲያጋድል አድርጎታል ማለት ነው ። ዳኞቹ ሁልጊዜ ለሹመትም ለስጦታም ወደ ንጉሡ የሚቀርቡት በእልፍኝ አሽከሮች አለቃ አማካይነት ስለሆነ በዚህ ዓይነት አፈራረድ አብዲናጎን ደጅ የጠኑ ይመስላል ።

ከሽምብራ ኩሬና ከአይፈርስ ጦርነት በኋላ የንጉሡ ጦር ተሸንፎ ሰው ሁሉ በመገረም ተስፋ በቆረጠበት ሰዓት ከግዛቱ የመጣው ራስ ወሰን ሰገድ በተሸነፉት ንጉሥ ዙሪያ ያሉትን መኳንንት በወቀሰበት ጊዜ «በምን የተነሣ እስላሞቹ እዚህ አደረሱ ችሁ ከናንተ በፊት አባቶቻችሁ በጀግንነት እየተዋጉ ይመልሷቸው ነበር ። ይኸ ሰውዬ (ግራኝ) በናንተ ላይ ያደረገውን እነዚያ ባባቶቻችሁ ላይ ከቶ አላደረ ጉባቸውም ። በጨካኝነታችሁና በሕዝብ ላይ በፈጸማችሁት ግፍ የተነሣ እግዚአብ ሔር እነዚህን ከአንበጣ በቀር (ለምግብ ?) የማያውቁትን አስነሥቶ አገራችሁን ደዋሮን ፈጠጋርን ከተሞቻችሁን ባደቄን አቃጠሉት . . . . . .» ብሎ የወረወረው ወቀሳ የቀድሞውን የመኳንንቱን ግፈኛ አገዛዝና ያሁኑን የእግዚአብሔርን ቁጣ ያሳያል (2) ። ንጉሡ ነገሥቱ ምንም እንኳ ደግነታቸው መንፈሳዊነታቸው የታወቀ ቢሆን በዚሁ የተነሣ መኳንንቶቻቸውን ከአጉል ፍርድና ከግፈኛ አገዛዝ ሊያግዷ ቸው አልቻሉም ይሆናል ። እርሳቸው ከመንግሥቱ ሥራ የተረፈውን አብዛኛውን ጊዜያቸውን ካህናትን ፤ ሊቃውንትን እየሰበሰቡ መንፈሳዊ መጻሕፍት በመመር መር ከካህናቱ ጋር በመጨዋወት እነርሱን በማብላት በማጠጣት ያሳልፉ እንደነ በረ ታሪካቸው ይገልጻል (3) ።

ድልወትና መለሳለስ ያበዛ ፤ አገዛዝ ያበላሸ ፤ ፍርድ ያጣመመ መንግሥት ሁሉ ባጭር ወይም በረዥም ጊዜ ውስጥ ከውድቀት አይዘልም ። ምንም አዋቂ ቢሆን

(1) የአልቫሬዝ መጽሐፍ በነአቶ ግርማ ትርጉም ገጽ 311 ። Portuguese Embassy = Lord Stanly ገጽ 318

(2) ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 221

(3) «ወንጉሥሰ መሣሐዊ ልብነ ድንግል ረሰየ ኵሎ ሑረቶ ኀበ እንብቦ መጻሕፍት እምላካውያት ወለብዎ ውሳጢያቲሆሙ ። ሰበኒ ይትፌሣሕ ይጼውዕ ካህናተ ወይዛዋዕ ምስሌሆሙ በነገረ መጻ ሕፍት እንዘ ያስተፌሥሖሙ በማኅሌት ወወይን ወያሠረግዎሙ በአልባሳት ቅድሳት . . . . . .» የልብነ ድንግል ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 8 ።

ድርጅቱ ወጉና ሥርዓቱ የበዛና ዕውቀቱም የረቀቀ ቢሆንም ይኸን የመሰለውን መንግሥት ዕውቀትና የተሻለ ድርጅት የሌለው የተናቀ ሕዝብ ባንድ ባልተጠበቀ ኃይል ሊገለብጠው ይችላል ። በዚህ ጊዜ ድርጅቱም ዕውቀቱም የመጻሕፍቱ ምር ምርና ሊቃውንቱም እራሳቸውንም መንግሥቱንም ሊያድኑ አይችሉም ።

በዘመናቸው እንደ ሮማውያን አዋቂዎች ፣ ደፋሮች ፣ ተዋጊዎች በዓለም አል ነበረም ። የእጅ ጥበባቸው ፣ የሕንፃ ሥራቸው በሮማና በገዙት አውራጃ ሁሉ የተ ዉት የአብያተ መንግሥትና የጣዖታት መቅደስ የሕንፃው ፍርስራሹ ዛሬ ለአገር ጐብኝ ዓይን ድንቅ ነው ። የግዛታቸው ስፋት ከእንግሊዝ አገር እስከ ፋርስ ከጀር መን አገር እንሥቶ ሰሜን አፍሪካን መካከለኛ ምሥራቅን ሁሉ ጠቅልሎ ከምዕራብ እስከ ሱዳን በምሥራቅ እስከ ዓረብ አገር እስከ የመን ደርሶ ነበር ። እኛ ከወረራ የተ ረፍነው በተራራችን ብዛት ይሁን ወይንም ተዘንግተን ይሁን ምስጢሩ በትክክል አይታወቅም ። የሆነ ሆኖ የቀረው ቢቀር አለመገዛታችን መሠልጠንን ያስቀረብ ንን ወደ ጐን አድርገን ዛሬ በትምክህት ለመጠቀም እንሞክራለን ።

በኋላ ግን የዚሁ የሮማ መንግሥት መሪዎች እንዳዬ ልብን ድንግል ዘመን ዘመናይነት ተድላና ደስታ ሲበዛ በነገር መራቀቅ በመብል በመጠጥ በሥጋ ፍትወት መደሰት ሲበረክት ቀድሞ ባሮች ወይም አረመኔዎች እያሉ በሚንቋቸው የጀርመን የቪዚጐት የቫንዳልና የፍራንክ ሕዝቦች ለመገልበጥ ቻሉ ። ይህ ሰፊው የሮማ ታሪክና ጠባቡ ያዬ ልብን ድንግል መንግሥት የውድቀት ታሪክ በመሠረተ ነገሩ ተመሳሳይነቱ በግልጽ ይታያል ። በመስቀል ጦርነት ጊዜ በነሳላህ ዲን የሚ መሩት ዓረቦች ቍጥራቸው የበረከተውን የአውሮፓ ነገሥታት በቅድስት አገር እንደምን እንዳጠቁዋቸው ከዚያ ወዲህ የአውሮፓ ነገሥታት እንግሊዝና ፈረን ሳዊ በምን አኳኋን ዓረቦች የተባሉትን ሁሉ እንደምን እንደገዟቸው በማንም ዘንድ የታወቀ ስለሆነ ለምሳሌ መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም ።

በዚህ ላይ የምንመለከተው ነዋሪ ገኘ ነዋሪ ተገኘ ፣ ዘለዓለም አሸናፊ ለዘለዓ ለም ተሸናፊ በምድር ላይ አለመኖሩን ራሷ ዓለም በፀሐይ ዙሪያ እንደምትዞር በላ ይዋ ላይ የሚቀመጠው ሕዝብም ኃይሉም ሥልጣኑውም እድሉም እንደቀለበት እየዞረ ሁሉም በየተራ የክብርና የኀሣርን ጽዋ እየተጻረሰ ከመቅመስ አለመዝለሉን ለሁሉ ጊዜ አለው የሚባለው ሰሎሞናዊ ፍልስፍና አነጋገሩ ቀላል ሆኖ ሳለ አፈጻ ጸሙ ከባድና መሠረት ያለው መሆኑን ነው ።

ባሁኑ ጊዜ የግራኝ አህመድ የጦር አለቆች አሸናፊዎች ፣ ደስተኞች እንደመሆ ናቸው መጠን ዓፄ ልብነ ድንግል ከነቤተ ሰባቸው ከነሹማምንቶቻቸው በመከራና በኀዘን ተውጠዋል ። ከአሥር ዓመት በፊት ይህ አልነበረም ፣ ከአሥር ዓመት በኋላ ደግሞ ሁለቱ ወገኖች ያሉበትን ሥፍራ ሲለዋወጡ ገዳዩና ገርግናው ግራኝ አህመድ በፋንታው ኩራትንና ቅምጥልነትን ከእየ በኋላ የሞትን ጽዋ ሲቀበል ይታያል ። አንዳንድ ጊዜ ይኸን የመለዋወጥ ዕድል ዕውቀትና ድርጅትም የሚመልሰው አይ መስልም ።

እስከዚያ ድረስ ግን የነዚህም ደስታ የነዚያም ኀዘን መቀጠል አለበት ። የንጉ

ሡና የቤተ ሰቦቻቸውም ሁኔታ በሚቀጥሉት ዓመታት እየባሰበት በጦርነት የሚሞ ተው ከጦርነት ላይ እየተማረከ ወደ ዓረብ አገር የሚላከው ቍጥር በየጊዜው እየ ጨመረ የቤተ አምሐራ የላስታና የኤርትራ ፣ የትግሬ አውራጃዎች በፈንታቸው የግራኝ ሰይፍ ሲጉበኛቸው ነገሥታቱ በየዘመናቸው ያሠሩት ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በረዥም ዘመናት ያደለቡት ሀብት እንዳለፈው ሁሉ እየተዘረፈ በእሳት ሲጋይ እንመለከታለን ።

ISIC

# ፬ኛ ክፍል
# ከሸዋ ወደ ቤተ አምሐራ መዛወር

## ምዕራፍ ፶፰
## የዓፄ ልብነ ድንግል ከወጅ ወደ ቤተ አምሐራ (ሐን) መዛወር
## (፲፭፻፳፫ ነሐሴ ፲፭፻፳፬ መስከረም)

ባለፈው እንደምናስታውሰው ራስ ወሰን ሰገድ በሞተ ጊዜ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድን ግል ከአዋሽ ወንዝ በስተደቡብ በወጅ ነበሩ ። የዚህም ወረዳ ገዥ የቆም ደሀር ልጅ እስላም ደሀር የሚባለው ነው ። በዚህ ወረዳ ሳሉ አሳዛኙንና አስደንጋጩን የራስ ወሰን ሰገድን ሞት ሰሙ ። እርሱ ተዋግቶ የሞተበት ሥፍራ ወደ ቦስት ተራራ አቅ ጣጫ ሲሄድ ስለሆነ እርሳቸው ካሉበት ከወጅ (ከዛሬው ወንጂ ?) ሩቅ አልነበረም ። ኮንቲ ሮሲኒ ወሰን ሰገድ ተዋግቶ የሞተበትን ሥፍራ ቆርቆራ ብለውታል ። በዚህ ዓይነት ቆርቆራ ወይም ቁርቁራ ቢሾፍቱ አጠገብ መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተ ናል (1) ። ይህ ታላቅ የጦር አለቃና የጠቅላላው ሕዝብ አባትና አለኝታ የተባለው መኰንን ሲወድቅ በዚህ ክፍል የጨካኙን ጠላታቸውን የግራኝን የጦር ኃይል ሊመክት የሚችል ምንም ኃይል እንደሌለ ንጉሡ ይገነዘቡታል ። ከርሱ ሞት በኋላ ወደርሱ የሚገባው እየበረከተ ሄደ ። የርሱ መሞት ተስፋ እያስቆረጣቸው ወደ ግራኝ ከዞሩት ውስጥ በበኩሉ ከፍ ያለ የጦር መሪ የነበረው የይፋቱ ገዥ አውራይ ኡስማን ከነጦሩ ፤ ከነሹማምንቱ ወደ ግራኝ የአገባቡን አኳኋን እንብበናል ። ከወ ሰን ሰገድ ሞት ቀጥሎ የአውራይ ኡስማንን ወደ ግራኝ ከነጦሩ መግባቱን ሲሰሙ በኀዘን ላይ ኀዘን እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ወደ አልተያዘው የአማራ አገር ከመንዝ በቀር ሌላ ምንም ለንጉሡ የቀራቸው ምርጫ የለም ። ቀድሞውንም ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር ሆነው በቁርጠኝነት ያላደረጉትን አሁን እርሱ ከሞተ በኋላ በእልህ አዋሽን ተሻግ ረው ግራኝን ጦርነት ቢገጥሙት ለመከላከል ባጠገባቸው ያለውን ወታደር ከማስ ጨረስ የራሳቸውንም ሕይወት ለሞት ወይም ለምርኮ አደጋ አሳልፎ ከመስጠትና በጥብቅ የሚፈልጋቸውን ጠላታቸውን ከመጥቀም በቀር ሌላ ረብ የለውም ።

በዚህ ምክንያት በዚሁ በዋናው ክረምት በነሐሴ ወር ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ከወሰን ሰገድ ሞት በኋላ ወጅ ከሚባለው ተነሥተው የአዋሽን ወንዝ ተሻግረው ያን ጊዜ የአማራ ግዛት በተለይ እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ወሲል እንደ ግዕዙ (ዋስል ምድረ ሐን) ይባል ወደነበረው ዛሬ ጋሎች ከተሠማሩበት ወዲህ ወረይሉ (ወረ ኢሉ ደሉ ካቢጭሳ ጋቲራጋ) ወደተባለው አመሩ ። ይህ ወረዳ ያን ጊዜ እንደ ዓረብ ፋቂህ

(1) Storia di Libne-Dingel ገጽ 16 ማስታወሻ ቍጥር 1 ።

ወሲል እንደ ግዕዙ ዋስል የሚባለው ሥራው በዘመኑ አስደናቂ የነበረው በምረቃው ቀን እነአልቫሬጽ የተገኙበት የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ያለበት ነው ። ከዚህ ከሸዋ ከግድምና ከመንዝ በሰላ ድንጋይ በኩል አልፎ ምቸግ ወደ ተባለው የተራራ በር ያደርሳል ። በግራ በኩል ደግሞ በመራቤቴ በኩል አድርጎ ዶባን አልፎ የአህያ ፈጅ ገደልና ተራራ ስለሚገኝ ንጉሡ እነዚህን በሮች አልፈው በሐን መቀመጣ ቸው በር በሩ በወታደር ከተጠበቀ ግራኝና ጦሩ ሊያልፍበት አይችልም ብለው ተስፋ አድርገው ነው ። ነገር ግን ለግራኝ አህመድ በዚያን ጊዜ ይኸን የመሳሰለው በርና ተራራማ ሥፍራ ሁሉ ሊያግደው ስለአልቻለ አሁንም ይህ ተራራማ ሥፍራ ሳያግደው እግር በግር የሄዱበትን ፈለግ ተከትሎ ሄዶ ሲያጠቃቸው እናነባለን ። እርሳቸውም እርሱም የሄዱበት የወረዳና የቀበሌ ስም የዚያን ጊዜና የዛሬው አጠ ራሩ አንዳንዱ መለያየቱን እንባቢ በየምዕራፉ ይገነዘበዋል ።

የራስ ወሰን ሰገድን ሞትና ያማራውን አገር ጉዞ ታሪከ ነገሥታችን እንደዚህ ሲል ጠቅሶታል «በነሐሴ ፲ ቀን ራስ ወሰን ሰገድ ሞተ ። ከዚያ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ንጉሡ ወደ አማራ አገር ሄዶ በሐን ተቀመጠ» (1) ። በሁለተኛው ዓመት ሲል ግዕዙ ወሰን ሰገድ በሞተ ባመቱ ወደ አማራ አገር እንደሄዱ ያስመስለዋል ። ዓረብ ፋቂህ ግን ወደ አማራ አገር ያደረጉት ጉዞ ወዲያው ወሰን ሰገድ በሞተበት ዓመትና ወር ያደርገዋል ። ሁኔታውን ሲመለከቱት ያረቡ ጸሐፊ ትክክለኛ ይመስ ላል ። ወሰን ሰገድ ከሞተ በኋላ የግራኝ ሥልጣን በተስፋፋበት በደቡብ ክፍል አንድ ዓመት ሊቀመጡ አይችሉም ። ስለዚህ ግዕዙ ከሁለት ዓመት በኋላ ብሎ መነሻ ያደረገው ምናልባት ንጉሡ ተዋግተው የተሸነፉበትን የሽምብራ ኩሬን ጦር ነት ፲፭፻፳፩ ዓ. ምሕረትን ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ሁኔታውን በትክክል መንገድ ከዚህኛው ባጭሩ ብቻ ከተጠቀሰው ከግዕዙ ይልቅ እንደተለመደው ዓረብ ፋቂህ ሰፋ አድርጎ ስለሚተርከው እርሱን በቀጥታ ከዚህ እንደሚከተለው ማንበቡ ይጠ ቅማል ።

«ይህ ሁሉ ሲሆን ንጉሡ ወናግ ሰገድ በወጅ አገር ክረምቱን ሁሉ አሳለፈ ። በዚሁም አገር ሳለ የወሰን ሰገድን ሞት በሰማ ጊዜ ታላቅ ኀዘን ተሰማው ። ከዚያ የጦር ሹማምንቱን ቤተ ሰቡን የቤተ መንግሥት አገልጋዮቹን ሰበሰበና እንግዲህ ምን ማድረግ ይሻላል ። እናንተስ ምን ትመክሩኛላችሁ ፤ የትኛውስ አገር ይቀበለ ናል ብሎ ጠየቃቸው ። የዚህኑ ነገር እያወጡ እያወረዱ ሲመካከሩ ከቆዩ በኋላ ቀጥሎ ንጉሡ ራሱ እንደዚህ አለ ። "ያባቶቻችን ያያቶቻችን የነገሥታት መደ በኛ ሥፍራ ወደ ሆነው ወደ ቤተ አምሐራ ሄደን በዚያ እንቀመጥ ። እስላሞቹ እስካ ሁን ድል የመቱትን አገር እንተውላቸው እኛ ግን ቤተ አምሐራ ሆነን በር በሩን ይዘን ከእስላሞቹ ጋር እየተዋጋን እንሙት" ።

ይኸን በተናገረ ጊዜ ሹማምንቱ ንጉሥ ሆይ እውነትህ ነው እዚያ ሆነን እየተ

(1) ወአመ ፲ቱ ለነሐሴ ሞተ ራስ ወሰን ሰገድ ። ወእምዝ በ፪ ዓመት ሐሰረ ንጉሥ ምድረ አምሐራ ወነበረ በሐን ። ታሪከ ነገሥት ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 328

ዋጋን እፊትህ እንሞታለን አሉት ። ከዚህ በኋላ በክረምቱ ጊዜያት ሳያርፍ ፩ ወር (ነሐሴ) ተጉዞ ቤተ አምሐራ ደረሰ ። ይኸውም አገር ሰፊ ተራራማ መንገዱ ጠባብ ነው ፤ ከተማው የነገሥታት መቀመጫ ነው ። ከዓባዊ (ዓባይ) ዠምሮ እስከ አን ጎት ሐይቅ ድረስ ኻያ ቀን የሚያስኬደው አገር በተራራ የተከበበ ነው ። ይኸውም አገር አንዱ በወለቃይ (ወለቃ) (1) ፤ አንዱ በአኪ አፋጂ ነው (2) ። አንዱ በመንዝ አንዱ በማያት አንዱ በግድም በኩል ፭ በር አለው ። ከነዚህም ውስጥ ተከላከል በዚህ በር ማንም መጥቶ አያውቅም ብሎ የማያትን በር ለአማቹ ለደገልሃን ሰጠው ። እርሱም የግድምን አጋማሽ የትግሬን ጦር ይዞ በመንገድና በተራራው በላይ በኩል በመንገድና በበሩ መካከል የሚያስፈራ ጉድጓድ አስቆፈረ ።

የመንዝን በር ለራስ ባንያት (ነቢያት) ሰጠው ። እርሱም በተራራው ላይ ጉድ ጓድ አስቆፈረ ። የአኪ አፋጂን በር ግን ለመከላከል ስድስት ሰው ብቻ ስለሚበቃ እንያዚሁ ተወው (3) ። የወለቃይን በር ዳህረጐት (ዳሀር ጎይታ) ለሚባለው ሰጠው» (4) ።

በዚህ ዓይነት ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ ዓፄ ልብነ ድንግል የመንግሥቱ መደብ የነበረውን ሸዋን ለግራኝ ለቀው ወደ ቤተ አምሐራ ሄደው ተቀመጡ ። ግራኝ ግን እንደማናቸውም ኃይለኛ አገር ወራሪ ድልም የምርኮ ሀብትም ሰፌ ግዛ ትም በቃኝ የማይል ሰው ስለሆነ በዚሁ በደቡብ አገር ይኸውም ማለት ከሺህ ሆጀሌ አገር ጀምሮ እስከ ይፋት ጫፍ ድረስ በወርዱም በስፋቱም በአሉት አውራ ጃዎች በሸዋ ፤ በፈጠጋር ፤ በደዋሮ ፤ በይፋት ፤ በባሌ ፤ በየአውራጃው ታማኞቹን በሹመት ከደለደለ ክርስቲያኑን ሕዝብ በመግደል እያስፈራራ በጅምላ ካሰለመ በኋላ በየጊዜው ድል አድራጊነቱና መስፋፋቱ እየጣመው አሁንም ንጉሡ ነገሥ ቱን በሄዱበት በቤተ አምሐራ እየተከታተለ ሲወጋቸው ወደፊት እንመለከታለን ። ዓላማው የመላዋ የኢትዮጵያ ጌታ ለመሆን ስለሆነ ከዚህ በፊት ማናቸውም የጦር ነት ችግር ክረምቱም ጫካውም ተራራውም እንዳላገደው አሁንም የአህያ ፈጅን ተራራና ለተከላካይ ምቹ የሆነውን በር በምን ዓይነት ዘዴ አልፎ ንጉሡ ካሉበት ደርሶ ከጦራቸው ጋር ተዋግቶ ከዚያም እንዳባረራቸው እናነባለን ።

(1) ወለቃ ከዛሬው ሰላሌ ሰሜን ከወረይሉ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ወረዳ ነው ።

(2) ዓረብ ፋቂሀ አኪ አፋጂ የሚለው ዛሬ አህያ ፈጅ የሚባለው መሆን አለበት ። ዛሬም ፋጂ አላይ ጨፌ ምችግ (ምሽግ) የሚባሉ ፫ የምክትል ወረዳ ግዛቶች በጂማ ወረዳ በወረይሉ አውራጃ ይገ ኛሉ ። ያገር ግዛት ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የጠቅላይና ያውራጃ የወረዳና የምክትል ወረዳ ዝርዝር ገጽ 14 ተመልከት ።

(3) የአኪ አፋጅን በር ለመጠበቅ ፮ ሰው ብቻ ይበቃል የተባለው በጣም ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ ነው። ይኸን ሥፍራ እንጋገሩን ባለ ማወቅ ወይም በዚያ ዘመን አነጋገር አኪ አፋጂ ይበለው እንጂ በዚህ ሥፍራ ከጦርነቱ አሥር ዓመት በፊት ፖርቱጋሎች በዚህ ቦታ ሲያልፉ በእጃችን እየቧጠጥን አለ ፍን ። በቅሎቻችንና ሰዎቻችን ሲያልፉበት ባላይ ኖሮ ፍየል እንኳን ያለ ሥጋት ያልፍበታል ብዬ አላምንም ነበር ። ስሙም አህያ ፈጅ ይባላል ሲል አልቫሬዝ በደንብ አብራርቶታል ። የአልቫሬዝ መጽሐፍ በነአቶ ግርማ ትርጉም ምዕራፍ 66 ።

(4) ዓረብ ፋቂህ . . . . . . . . ገጽ 281 - 282

ISIC

የሆነ ሆኖ በራስ ወሰን ሰገድ ሞት በግራኝ አሸናፊነትና መስፋፋት ይልቁንም
ፀዌ ልብነ ድንግል ሸዋን ለቀው ወደ ቤተ አምሐራ በመሄዳቸው በኢትዮጵያ
ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ ። ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ዓፄ ልብነ ድንግል በሕ
ይወታቸው ወደዚህ ወደሸዋና ወደ ደቡብ እንደገና በፍጹም አልተመለሱም ።
ምንም እንኳን እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ልጆቻቸው እነዓፄ ገላውዴዎስ የልጅ ልጆ
ቻቸው እነዓፄ ሠርጸ ድንግል አገር ለማቅናትና ግዛት ለመጠበቅ ያህል መምጣታ
ቸው ባይቀር በጠቅላላው ሸዋ የነገሥታቱ መቀመጫ መሆኑ የቀረው ወይም መቅ
ረቱ የተወጠነው ዓፄ ልብነ ድንግል በዚህ በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ወደ ቤተ አምሐራ
ከሄዱ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል ።

መዠመሪያ የዮዲት መነሣት ለዛጕዬ መንግሥት መቆምና ለላሊበላ ከተማ
መፈጠር ምክንያት ሆኖ የአክሱምን መደበኛ ከተማነት እንዳስቀረው ቀጥሎ በይ
ኵኖ አምላክ መሪነት የአማሮቹ መነሣት የዛጕዬን መንግሥታዊ አቅዋምና የላሊበ
ላን ንጉሣዊ ከተማነት እንደሻረው አሁን ደግሞ የግራኝ መነሣት የሸዋውን የነጋ
ሢዎች መደበኛ ሥፍራነቱን አስቀርቶ ለጐንደር ከተማ መፈጠር አዲስ የታሪክ
በር ከፈተ ። የጐንደር ከተማ የተቆረቆረው በኋላ በፋሲል ዘመነ መንግሥት መሆኑ
ቢታወቅም ለዚህ ሁሉ ምክንያት ያቀረበ የግራኝ አነሣሥና ያፄ የልብነ ድንግል
በሸዋ ተሸንፈው ወደ ቤተ አምሐራ ከነንጓዛቸው መዛወር ነው ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ይህ አሁን ዓፄ ልብነ ድንግል የሄዱበት ቤተ
አምሐራ የተባለው አገር የሥርወ መንግሥቱ (ዲናስቲው) መሥራች ዓፄ ይኵኖ
አምላክ ተወልዶ እየተማረ ያደገበት (ሐይቅ እስጢፋኖስ) አማሮች በጥንቱ ዘመን
የተተከሉበት የሥሪት አገራቸው ስለሆነ ፈላሾች ወይም እሥራኤላውያን ያሉበት
ቤተ እሥራኤል እንደሚባለው ሁሉ ይኸም አውራጃ ቤተ አምሐራ ሲባል ይኖር
ነበር ። በምዕራፍ ፩ ገጽ ፲፫ ላይ እንደተመለከትነው ይኵኖ አምላክ በዚሁ ወረዳ
ተነሥቶ እዚህ ባሉትና ሸዋ ባሉት የነገድ ወገኖቹ በአማሮቹ እየተረዳ መንግሥትን
ከዛጕዬዎቹ ወስዶ ከ፲፪፻፷፪ ዓ. ም. ዠምሮ በሸዋ ሲመሠረት ከዚህ ጊዜ ዠምሮም
የአማሮቹ ቋንቋ አማርኛ የመንግሥቱ ቋንቋ ሆኖ አብሮ የተመሠረተው እነሆ
እስከ ጊዜያችን ደረሰ ። አሁንም ዓፄ ልብነ ድንግል እንደ ዕድል ሆኖ በዘመናቸው
ይህ የጦርነትና የመከራ ፍዳ ደርሶ ደቡቡን ሁሉ ግራኝ ሲይዘው «እንግዲህ ምን
ይደረግ ወደ እያቶቻችን ወደ አባቶቻችን አገር ወደ ቤተ አምሐራ እንሂድ» ያሉት
ሰው ዞሮ ዞሮ ይኸን በመሰለ የመከራ ጊዜ ለመከላከልም ሞቶ ለመቀበርም ቢሆን
ከሥር የትውልድ አገሩን ስለሚፈልግ ነው ።

ስለ ቤተ አምሐራ የዓረቡ ጸሐፊ በዘመኑ የሰማውንና ባይኑ ያየውን እንደዚህ
ብሎ ጽፎአል «ቤተ አምሐራ የሚባለው አገር በዝናምና በወንዝ ውሀ እየተጠቀመ
ገብስና ስንዴ የሚያበቅል አገር ነው ። በዚህም አገር የክርስቲያን ሊቃውንት ቀሳ
ውስት መነኮሳት ይቀመጡበታል ። ለዘለቄታም ባይሆን ንጉሥ የሆነው ሁሉ ብዙ
ጊዜ እየሄደ ይቀመጥበታል ። የቤተ አምሐራ ሊቃውንትና ቀሳውስት ሳያጸድቁት
ንጉሥ አይባልም ። አገሩ የካህናት አገር ነው እነርሱም በንጉሡ ዘንድ የተከበሩ አን

ጳንዶቹም ዘመዳሞችና መሪዎች ናቸው» (1) ።

ይኸን የዓረቡን አጻጻፍ የመካነ ሥላሴው ተወላጅ የዮብ ሩዶልፍ ግዕዛዊ መምህር ጐርጐርዮስ የሚባለው በ፲፮፻፶ ዓ. ም. ላይ ለሳክሶን መስፍን ለኤርኒስቶ ሲጽፍ በግዕዝ እንደዚህ ሲል አጽድቆታል «ትውልዴ ከቤተ አምሐራ ነው ። ይኸም ነገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የበላይ ነው ። የዚህ ነገድ መኳንንቱ መሳፍንቱ ነዋሪ አማካሪዎቹ ፤ ከንጉሡ በታች ሆነው የሚሾሙ ፤ የሚሽሩ ፤ የሚያዙ ፤ የሚገዙ ናቸው» (2) ። በጠቅላላ አነጋገር ለማለት ካልሆነ በቀር በንጉሥ ነገሥቱ ምርጫ ከማናቸውም ከኢትዮጵያ ያውራጃ ነገድ እንደ ዛሬ ያንጊዜም ማናቸውም ተወ ላጅ በታማኝነቱና በአገልግሎቱ ከፍተኛ ደረጃ በመያዝ ከአማሮቹ ባለሥልጣኖች ጋር ተሰባጥሮ እንደሚሠራ የታወቀ ስለሆነ ራሱን ለማክበሪያ ጭምር ያመጣው የጐርጐርዮስ አጻጻፍ ሙሉ ለሙሉ ላይታመን ይችላል ።

ይሁን እንጂ የመንግሥቱ መደበኛ ሥፍራ በሸዋ ደብረ ብርሃን (ተጉለት) በሬ ጣጋር (የረር ቦካን ባደቄ ሽምብራ ኩሬ) ቢሆንም ካዬ ይሥሐቅ አምላክ እስካሁን እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ድረስ (፲፬፻፷፪ - ፲፭፻፴፩ ዓ. ም.) ዓረብ ፋቂህ እንዳለው ነገሥታቱ በየጊዜው ወደ ቤተ አምሐራ እየሄዱ ቤተ መንግሥት በዚያም ጐን ቤተ ክርስቲያን በየስማቸው መትከልን እንደልማድ አድርገው ይዘውት ይኖሩ ነበር ። በዚህ ምክንያት ዓፄ ሰይፈ አርእድ ደብረ እግዚአብሔርን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደብረ ነጐድጓድን ዓፄ በዕደ ማርያም አትሮንሰ ማርያም 131C ዓፄ እስክንድር ገነተ ጊዮርጊስን ሌሎቹም በየቦታው እየተከሉ በነዚህ አብያተ ክርስቲያን ላይ የሚሾሙት አለቆች የተከበሩና የተማሩ ከፍ ያሉ ሊቃውንት ናቸው ። ለምሳሌ አትሮንሰ ማርያምን ዓፄ በዕደ ማርያም ተክለው ለዚህ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ዓምዱ የተባለውን መርጠው "መክብበ አትሮንሰ ማርያም" ብለው የሾሙት ጊዜ የሚለብሰው በወርቅና በብር ያጌጠ ካባ ፤ በራሱ ላይ የሚደፋው የወርቅ አክሊል ፤ ከራሱ በላይ የሚያዝለት ድባብ ፤ መስቀል ይዘው የሚያጅቡት ፤ የሚበላበት ገበታና የሚጠጣበት ብርሌ ሳይቀር ተደንግጎ ተወስኖለታል (3) ።

ከሁሉ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ባሁኑ ጊዜ ብልጫ ያለው እላይ የጠቀስነው ታቦቱ የገባ ለት እነአልቫሬጽ በሥፍራው ተገኝተው ያከበሩት የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነው ። አሁን ግራኝ ንጉሡን በሚያሳድድበት ጊዜ በሚያሳዝን አኳኋን እነዚህን ሁሉ እያቃጠለ አመድ ሲያደርጋቸው እንመለከታለን ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 306 - 307
(2) ሙላደ ዚአየሂ እ ፍቁርየ ኢይምሰልከሙ እምነ ሰብእ ንኡሳን አላ እምቤተ አምሐራ ውእቱ ። መኳንንቲሁኒ ወመሳፍንቲሁ ነገድ ክቡራን ዘውእቶሙ አርእስቲሆሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ ። መኳንንቲሁኒ ወመሳፍንቲሁ ወመናብርቲሁ ወመማክርቲሁ ለንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እለ ይሠይሙ ወይስእሩ ይኤዝዙሂ ወይመልኩ እምታሕቴሁ ለንጉሥ . . . . . . Historicam Aethiopicam Commentarius–Job Rudolphe ገጽ 28
(3) ያዓ ዘርዓ ያዕቆብና ያዓ በእደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 119 - 122 በየሥፍራው ።

## ምዕራፍ ፶፱

## በማያት (ቤተ አምሐራ) የአዛዥ ደገልሃን ውጤት ያለው መከላከልና አዘንጊ ድል አድራጊነት (መስከረም - ጥቅምት ፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ዓፄ ልብነ ድንግል ከሸዋ ወደ ጥንታዊው ያባቶቻቸው አገር ወደ ቤተ አምሐራ ደር ሰው በተለይ ሐን በሚባለው ሥፍራ መቀመጣቸውን ፤ ጦራቸውን በየበሩ ከሦስት ላይ ከፍለው አንዱን በማያት በኩል ወደ ቤተ አምሐራ የሚያስገባውን በር ለአማቻቸው ለአዛዥ ደገልሃን ፤ ፪ኛውን የመንዝ በር ለራስ ነቢያት ፫ኛውን የአህያ ፈጅን (አኪ አፋጂ ?) በር ለዳሀረጐት (ደሀር ጎይታ) እየደለደሉ መስጠታቸውን ባለፈው ምዕራፍ አንብበናል ።

የንጉሠ ነገሥቱም አሳብ እንግዲህ በዚህ በደቡብ ክፍል የግራኝ አሸናፊነት ስለተረጋገጠ በዚህ በዋሰልና በቤተ አምሐራ አገሩ ተራራማ ስለሆነ በአህያ ፈጅና በምኝግ በሌላውም በየበሩ ወታደር አስቀምጠው እየተከላከሉ ለመኖር ነው ። ዳሩ ግን በፊት እንዳልነው በአሁኑ ሰዓት በአሸናፊው በግራኝ አጠገብ በያይነቱ የወታደሩ ፤ የሹማምንቱ ፤ የነፍጠኛው ፤ የመድፈኛው ፤ የሰይፈኛው ፤ የቀስተኛው ቍጥር ከልክ እያለፈ እየበረከተ ሄዷል ። ከራሱ የዓረብና የአዳል ፤ የሱማሌ ወታደር ሌላ እስላም ነክነት ካለው ከደዋሮ ከባሌ ከይፋት ጦር በቀር ክርስቲያኑም የንጉሡና የጦር አለቆቻቸው በያለበት መሸነፍ ተስፋ እያስቆረጠው ከልቡም ያለልቡም ገብቶ የግራኝን ኀይል በዚህ ጊዜ አደርጅቶታል ። በዚሁ ዓይነት መንገድ መሪው መላ ፈጣሪው ወሬ ነጋሪው እየበረከተለት ሄዷል ።

ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ የትግሬውና የእንጐቱ ገዥ በአይፈርስ ተዋግቶ የሞተ ለት የተማረኩ የቤተ አምሐራ ሹማምንት በነፃነት ወይም በምርኮ ስም ከግራኝ ጋር ባሁኑ ጊዜ እንደሚኖሩ እነርሱም የቤተ አምሐራን መውጫ መግቢያ እንደሚያውቁ አይጠረጠርም ። ማወቃቸውንም ሌላው ይጠቁማል ። የሚያውቁትንም ሲጠየቁ ለመደበቅ ቢሞክሩ ለሕይወታቸው አደጋ ነው ። በእንደዚህ ያለው ጊዜ ላስተናብር ፤ ልምራ ፤ ልጠቁም ባዩ አገልግሎቱንና ገርግንነቱንም ላዲሱ ጌታ ላሳይ የሚለው አድር ባይ ብዙ ስለሆነ በእንደዚህ ያለ ጊዜና ሁኔታ በዚህ ሥፍራ እየተከላከሉ ብዙ ጊዜ በመቆየት ረገድ ዓፄ ልብነ ድንግልና ጦራቸው ያላቸው ተስፋ የደከመ ከመሆን አይዘልም ።

ስለዚህ ከነዚሁ ውስጥ እንደ እናንያ ያለው ከሐዲ ክርስቲያንና ረዳት መስሎ በጉዞ የደረሰበትን ባላገር የንጉሡን ወሬ በመጠየቅ እያታለለ እንደምን አድርጎ የግራኝን ጦር ወደ ተራራው እንደመራ ወደፊት ስናነብ ይህ ሰው ምን ያህል ወገኑን ጐድቶ የወገኑን ጠላት እንደጠቀመ እንመለከታለን ። የይሁዳን አከዳድ የሚያውቀው ክርስቶስ የሰው ጠላቱ ቤተሰቡ ነው ያለው አምላካዊ ቃል በዚህ ሰውዬ ላይ በግልጽ ይታያል ። ይሁዳስ በሠራው ተጸጽቶ ራሱን ገድሏል ። እናንያ ግን ግራኝን እስከ መጨረሻ ያለ ጸጸት ስላገለገለ የከሐዲነቱ መጠን ከይሁዳ ይብሳል ።

ከግራኝ አህመድ ጋር የነበረው ታሪክ ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ የንጉሡን ወደ

ISIC

ቤተ አምሐራ መሄድ ከተረከልን በኋላ በዚያ የተደረገውን መከላከልና እጥቂነት ከዚያው ከቆመበት አከታትሎ የሚተርከውን በራሱ አጻጻፍ ትርጉሙን ከዚህ እንደ ሚከተለው እንመልከት ።

«ንጉሡ ወናግ ሰገድ ጦሩን በየበሩ ከደለደለ ወዲህ ወደዚች (መካነ ሥላሴ) ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ውስጧን ግራና ቀኝ ተመለካከተና "እዩ እስላሞቹ ይችን ቤተ ክርስቲያንና የነገሥታት መቀመጫ የሆነችውን (አገር) ሊያቃጥሏት ይፈል ጋሉ" ብሎ ቢናገር "ንጉሥ ሆይ እስላሞች መጥተው ይቺን ቤተ ክርስቲያን ያቃ ጥላሉ ብለህ አትጨነቅ . . . . . . ስለርሷ እየተዋጋን እንሞታለን" አሉት እርሱም እንደዚህ ከቆረጣችሁ ደግ ነው በራችሁን ተጠንቅቃችሁ ጠብቁ ብሏቸው እነሱም እሺ ብለው በየክፍላቸው ተለያይተው ሄዱ ። ንጉሡም ወደ ወሲል ሄዶ በሩን ይዞ ተቀመጠ ።

ይማም በዚህ ጊዜ ጎይታ ኑርን ልኮ በግድም ውስጥ (ቂሳያህ) ያለችውን የጥ ንት ነገሥታት ያሠሯትን ቤተ ክርስቲያን አቃጠለ ። በውስጧም ሺ መነኮሳት ይኖሩ ነበር ። ቀጥሎም ይማምና አብጃድ ወደ ቂሳያህ (ግድም) ሄዱ ከክርስቲያኖ ቹም ወገን ወሰን ዣን የሚባል ፩፻ የእግረኛ ጦር ባለነጭ ጋሻ የሚባሉትን እንደ ያዘ ሁሉም ወደ ይማም ገብተው ሰለሙ ። በዚሁ ጊዜ አንድ ንጉሡ አክብሮ ያስቀ መጠው እስላም በአርሹናህ ነበር እርሱም እስላም ሆኜ ንጉሡን በማገልገል እንዳ ይቀጣኝ እፈራለሁና ከይማም ዘንድ ለሕይወቴ ISIS ረጋገጫ አስጠኝ (አማልደኝ) የሚል ቃል አሲዞ ለሕግ አዋቂው ለአቡበከር ኤል አርሹኒ ላከ ። አቡበከርም ወደ ይማም ገብቶ ተነጋግሮ ቃል ተቀበለለት ። ይማምም ያገሩን ሰው ከቢር ኑርን ላከለ ትና ከርሱ ጋር ሆኖ ይህ ሻፉ የሚባል እስላም ወደ ይማም መጣና ለንጉሡ ይገቡ የነ በሩትን የሚያማምሩ በቅሎችና ገጸ በረከት ለይማም አቀረበለት ። በዚህ ጊዜ ይማም ንጉሡ ወዴት ነው ያለው ብሎ ቢጠይቀው በቤተ አምሐራ ነው ያለው በዚያ ጦሩን ከፋፍሎ በር በሩን ይዞ ተቀምጧል ። ንጉሡ ራሱ የወሲልን በር ይዞ የማያትን ለአማቹ ለራስ ደገልሃን ሰጥቶታል ። ደገልሃንም ወደኔ እንድትመጣ ብሎ ልኮብኝ ነበር ነገር ግን የናንተን ወደዚህ ቂሳያህ (ግድም) መምጣታችሁን ስለሰማሁ ወደዚያ መሄዴን ትቼ ወደዚህ መጣሁ ብሎ መለሰ ።

በኛና ንጉሡ ባለበት መካከል ርቀቱ ስንት ይሆናል ብሎ ቢጠይቀው ንጉሡ ያለበት ፯ ቀን ፤ ደገልሃን ያለበት ፬ ቀን ያሳሄዳል ። ራስ ባንያት ያለበት ይኸን እስ ፈሪ ተራራ አልፎ ባንድ ቀን ጉዞ ይደረሳል ሲል መለሰ ። ይማም ይኸን ሁሉ ሰምቶ ከተረዳ በኋላ አገሩን ትተህ በፍጥነት ወደኔ ና ታስፈልገኛለህ ብሎ ወደ ኤሚር አሊ ላከ ። ቀጥሎም ጦር ጨምረህ ላክልኝ ብሎ ለወዚር አዶሌ እንደዚህ ሲል ደብዳቤ ጻፈለት ።

"በመሐሪውና በይቅር ባዩ በእግዚአብሔር ስም ለዓለም ጌታ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፤ ሰላምና ደህንነትም ለጌታችን ለመሐመድና ለቤተ ሰቡ ይሰጠው።

የተላከ ከአህመድ ቤን ኢብራሂም የእስላሞች ይማም ስለሃይማኖቱ የሚዋጋ ይድረስ ከወዚር አዶሌ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ከርሱም በቀር ሌላ (አም

ላክ) የለምና ቡራኬና ሰላም ከእግዚአብሔር ለነቢዩ ለመሐመድ ይሰጠው ።

አሁን ያለነው ግድም ውስጥ ከቂሳያህ መሆኑን ዕወቅ አዶሌ ሆይ ። ንጉሡ ወናግ ሰገድ ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ ጦሩን ከፋፍሎ በሩንና መንገዱን ዘግቶ ይጠብቀናል ። ኤሚር አሊ ወደኔ እንዲመጣ ትእዛዝ ጽፌለት ነበር ። መልሰም አላከብኝ ያለበትንም ሥፍራ አላውቅም ። ከኔ ጋር ያለው ወታደር ትንሽ ነውና ኤሚር አቡበከርን ኤሚር ሙጃሂድን ፪፻ ፈረስ አድርገህ የእግረኛ ጦርና የባሕርን ተዋጊዎች (ከዓረብ አገር የመጡትን መድፈኞች) እንድትልክልኝ ይሁን ላንተና ካንተ ጋር ላሉት እስላሞች ሁሉ ሰላም ይሁን ።”

መልዕክተኛው ያለዕረፍት ሌትና ቀን ተጉዞ በአሥረኛው ቀን ዘቃላ (ዝቋላ) ደርሶ ደብዳቤውን ለወዚር አዶሌ ሰጠ ። እርሱም እስላሞችን ሁሉ ሰብስቦ ደብዳቤውን አነበበላቸው ። ከዚያ ፪፻ ፈረሰኛ ፭፻ እግረኛ የባሕር ወታደር ሌላም ቀጥራቸው የበረከተ ነገድ ጨምሮ አቡበከርንና ሙጃሂድን የበላይ አድርጎ . . . . ወደ ይማም ላካቸው ።

ይማም እነርሱን ሲጠብቅ በቂሳያህ አንድ ወር ከአሥር ቀን የተበተነውን ወታደሩን እየሰበሰበ ተቀመጠ ። በመዠመሪያ ሻምሱ ፲፭ ፈረሰኛ ሺ እግረኛ ይዞ ደረሰ ። ኤሚር አሊ (ፋራቃሃም) ግን በተጉለት በወግዳ በሙገር እየተዘዋወረ ቆይቶ በኋላ ደብረ ብርሃን ሆኖ የይማምን ወሬ ለመጠየቅ ወደ ይፋት ሰዎች ላከ ፡ ከዚያ ISIC ከደብረ ብርሃን ተነሥቶ በ፲፭ኛው ቀን ደረሰ . . . . . . ከዚህ በኋላ ኤሚር አቡበከርና ጓደኛው ጦራቸውን እንደያዙ በሰልፍ ገብተው ከይማም ተገናኙ ይማምም እንደ እንግዳ አክብሮ በደስታ ተቀበላቸው . . . . . . ከዚያ የንጉሡን ነገር አንሥተው ሲነጋገሩ ቆይተው በመጨረሻ የቀሩትንም ሰብስቦ አሁን ይኸው ጦራችን ተሰብስቧል ፤እንግዲህ ስለቤተ አምሐራ ምክር አምጡ እኔ ግን ንጉሡን ለመውጋት ቆርጫለሁ አላቸው ። ከቢር መሐመድ ሁላችንም ወደ ቤተ አምሐራ ለመሄድ ተዘጋጅተናል ነገር ግን በኋላችን ያለው የሾገራህ (ሾጃራህ?) አገር እስላም ከሆነ ጥቂት ጊዜ ነው ሰው ሳንተው ሁላችንም ወደ ቤተ አምሐራ የሄድን እንደሆነ ወዲያው እስላምነታቸውን ይተዋሉ ። አሁንም ወይ እኔ ወይም ሻምሱ ወደዚያ አገር እንድንመለስ ያስፈልጋል ቢል እውነትህ ነው አሁንም በቅርብ ቀን ወደ እስልምና የዞሩትን ሰዎች ብቻ ይዘህ ወደዚህ አገር ተመልሰህ ጠብቅ ከአገራችን ከመጡት የጥንት እስላሞች አንድም ካንተ ጋር አይሂድ ብሎ መርቆ ሰደደው (1) ። ከቢር መሐመድ ወደ ሾጃራህ ከተመለሰ በኋላ አንድ ሰው ወደርሱ መጥቶ ሻምሱ አቃጠለው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ንጉሥ እስክንድር አስቀምጦት የነበረ ወርቅ አለ ፡ መንገዱንም እነዚህ ካንተ ጋር የተሰለፉት ሰዎች ያውቃሉ ብሎ በእጁ አመለከተው ከቢር መሐመድም እነዚህኑ ሰዎች ይዞ እያጉላላ ፲፪ ጠፍጣፋ ወርቅ ተቀበላቸው ። ቀጥሎም ሌላስ ያለ የምታውቀው የለህምን ብሎ እንደገና አንዱን ቢጠይቀው

(1) ዓረብ ፋቂህ ሾገራህ ያለው የሚገኘው በደብረ ብርሃን አጠገብ ነው ካለ በሸዋ ውስጥ ከይፋት የጣ ይርቀው የወገራን አገር ይሆናል ። ሌላ መገራ ደግሞ ሊኖር ይችላል ።

እዎን ፺፱ የወርቅ ጥፍጥፍ እያንዳንዱ መቶ ወቄት የሚከብድ ሁለት ትልልቅ ጥምዝ ወርቅ አለ ብሎ ነገረው ።

ከቢር መሐመድም እነዚህኑ ሰዎች የቀረውንም ወርቅ አምጡ ብሎ አዘዛቸው እነርሱም እሺ ብለው ሲመካከሩ ንጉሥ እስክንድር ለቤተ ክርስቲያን የሰጡትን ይኽን ወርቅ አስረክበን በኋላ እስላሞች ወደ አገራቸው የተመለሱ ወይም እዚሁ ሞተው ያለቁ እንደሆነ ንጉሡ አምጡ ብለው ይቀጡናል ስለዚህ ይኽን ሰው (ከቢሩን) ለመግደል ብልሃት እንፍጠር በዚህም ነገር ጓደኞቻችን እንዲረዱን እንላክባቸው ተባብለው ተስማሙ . . . . . ከዚያ ውስጥ ውስጡን ለወገኖቻቸው ልከው በጫካ ያሉትን ክርስቲያኖች ጠቀሷቸው እነሱም ከተራራ ወርደው ሲመጡ ታዩ ከቢር መሐመድም እነዚህ ምንድናቸው ብሎ ቢጠይቅ አንተን ሊወጉ የሚመጡ ክርስቲያኖች ናቸው ብለው ወገኖቹ ነገሩት ። ከዚህ በኋላ ፈረሱን አስጭኖ ወታደሮቹን ይዞ ወደነዚያ ሄዶ ሲዋጋ . . . . . ሞተ ።

ይማም ግን ከቂሳያህ ተነሥቶ ከሁለት ቀን በኋላ ጋንቡራ ደርሶ ሠፈረ (1) ። ከዚያም ተነሥቶ ከሁለት ቀን በኋላ ማያት ደርሶ ደገልሃን ወደሚጠብቀው በር ተጠጋ ። ደገልሃንም እስላሞቹን ሲያይ ጦሩን በተራራ ላይ አሰለፈ መለከቱንም አስነፋ ወርዳችሁ ተዋጉ ብሎ መርዝ ባለበት ቀስት የሚዋጉትን ወታደሮቹን አስቀደማቸው ። ይማም ወደተራራው ተጠግቶ አንዲት ዛፍ ሥር ቆሞ እግረኛን ብቻ ሊያስሄድ የሚችለው መንገድ አንድ ብቻ መሆኑን እያየ ይደነቅ ነበር ። በተራራውም ላይ ያለው የእህል አዝመራ ይታይ ነበር ። በዚህ ጊዜ ይማም ሳያውቅ ያንድ ክፍል የእስላም የእግረኛ ወታደር ወደ ተራራው ወጥቶ ጦርነቱን ከክርስቲያኖቹ ጋር ዠመረ ከነርሱም ጋር በቀስት መዋጋት የሚችሉ የዓረብ ወታደሮች እነአብድ ሳሌም . . . . . . ነበሩ ወዲያውም እስላሞቹም ክርስቲያኖቹም ቀስት እየተወራወሩ የቀስት ጦርነት ተዠመረ ። ወዲያው ቀስ በቀስ እየተጠጋጉ በመጨረሻ ተደበላልቀው ይዋጉ ዠመር ። አብድ ሳሌምና ጓደኛው አልሐጅ ከጓደኞቻቸው ጋር ሆነው በዠግንነት ተዋጉ . . . . . . ከእስላሞቹ ውስጥ አቡን የሚባለውን ከላይ ክርስቲያኖቹ የለቀቁት የድንጋይ ናዳ ራሱን ፈጥፍጦ ገደለው ። . . . . .

ይማም እሥር ሆኖ ወደ ተራራው ሲመለከት እስላሞቹ አጉል ቦታ ሆነው ከክርስቲያኖቹ ሲዋጉ ተመለከተና ማን ተዋጉ አላቸው ብሎ ተቆጥቶ አስመለሳቸው ። እነሱም የአቡንን ሬሳ ተሸክመው ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ ይማም ወደ ሠፈር ተመልሶ አውራይ ኡስማንንና ሌሎቹንም መንገድ መሪዎች አናንያን ፤ ሃይቤን ፤ አይበስ ለሐፄን ሰበሰበና ምክር እንዲሰጡት ጠየቃቸው ። ከነዚህ መካከል አይበስ ለሐፄ እንደዚህ ብሎ ተናገረ ፤ "እንግዲህ ተራራውና አስቸጋሪው መንገድ እነሆ ይኸው በፊታችን ነው ። ፈረስ የሚያስሄድ መንገድ የለም ። በእግራችን እንውጣ ብትሉም አይቻልም ። ወጥታችሁ በእግዚአብ

(1) ጋንቡራህ በግድም ውስጥ መሆኑ ሲታወቅ በዚህ ወረዳ በዚህ ሥያሜ ቀበሌ መኖሩን አላረጋገጥም ።

ሑር ፈቃድ አዝማቹን (ደገልሃንን) ብታሸንፉትም ከዚያ ቀጥሎ ከቤተ እምሐራ ወዲህ እስቸጋሪ መንገድና ወንዝ አለና ንጉሡ ወደአሉበት ወደቤተ እምሐራ መሄድ አትችሉም ። እንደኔ አሳብ የሆነ እንደሆነ ደገልሃን የያዘውን ይኸን ተራራ መውጣት ይቅርና ንጉሡ ወደ አሉበት ወደ ዋስል በር ሂዱ ። በዚያም ሄዳችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያሸነፋችሁ እንደሆነ ከዚያ ወዲያ የቤተ እምሐራን መንገድ የሚዘጋባችሁ የለም ። ንጉሡም ከተሸነፉ ወዲያ ደገልሃን ብቻውን እዚህ ቢቀመጥ የሚጠቅመው ነገር የለም ስለዚህ ይኸን የምሰጣችሁን ምክር ብትቀበሉ ይሻላል ።''

እርሱ ተናግሮ ሲጨርስ አናንያ አይበስ ለሐቄ ይኸን ምክር መናገሩ እውነት አለው አሁን ባለንበት ተራራ ፈረስ የሚያስሄድ ምንም መንገድ የለም ። ንጉሡ ያሉበት የዋስል ተራራ ፈረስ ሊወጣበት ይችላል ብሎ ተናገረ ። . . . . . ይማምና የጦር አለቆቹ እውነት ነው ብለው በዚሁ ተስማሙ ።

በዚሁም ሌሊት ክርስቲያኖቹ እየወረዱ ሱማሌዎች ባሉበት ወገን መውጋት ዠምረው ነበር ። ነገር ግን ሹሙ ማታን በፈረሱ ሆኖ እየወጋ ወደተራራቸው መለሳቸው ። ክርስቲያኖቹ ወደ ተራራው ከተመለሱ በኋላ ደገልሃን ለንጉሡ እንደዚህ የሚል ደብዳቤ ጻፈ ''ይማም ጦሩን ይዞ ወደኔ መጥቶ ተዋጋን ፩፻፶ የእግረኛ ወታደሩን ገደልሁበት ፤ ፴ ፈረሶቹን ማረክሁ እስላሞቹ ከተራራው ላይ ተመልሰው ሲወርዱ ሌሊቱን የትግሬ ቀስተኛ ወታደር ልኬ ከነርሱ ጋር ተዋግተው ብዙ ሰው ፈጇባቸው ። ከእንግዲህ ወዲያ እስላሞቹ ወደ ፈጠጋር ይሸሻሉ እንጂ አይመከቱም ።''

ISIC

ይኸን መልእክት ሁለት ሰዎች በግሥጋሤ ወስደው ለንጉሡ ሰጡት ። ንጉሡም የተሰጠውን መልእክት ተመልክቶ ታላቅ ደስታ ተሰማው ። ዘውዱንም ደፍቶ እዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የጦር አለቆቹን ሰብስቦ ይኸንኑ ገለጸላቸው ። ነጋሪትና መለከት እየተነፋ አለቆች መስቀልና (ጌታችንና) ማርያም በጠላቶችህ ላይ ድልን ሰጡህ እያሉ አመሰገኑት ። ንጉሡም አማቹ ደገልሃን የጠበቅሁትን (ድል) ፈጸመ እያለ ሁለት ቀን በደስታ ውለው አደሩ ። ይሁን እንጂ ይኸ ሁሉ ውሸት ነበር ። . . . . .» እያለ የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ይተርካል (1) ።

መቼም ከአራት ዓመት ዠምሮ በተደረገው በደዋሮ ፤ በባሌ ፤ በፈጠጋር ፤ በዳሞት ጦርነት ሁሉ ግራኝ ከነጦሩ አጥቂ አሳዳጅ አሸናፊ ማራኪ አስገባሪ እንደመሆኑ መጠን ክርስቲያኖቹ ተጠቂ ተማራኪ ተሸናፊ ሆነው ስለቆዩ ንጉሡም ሹማምንቱም የአንድ ቀን እንኳን የድል ጮራ እንደሚናፍቃቸው የታወቀ ነው ። ደገልሃንም ወዲህ ጠቅላይ የጦር አዛዥ (መልአከ ኃይል) ወዲህ የንጉሡ አማች በመሆኑ ያለፈውን የመሸነፍ ሐሜት ለማደስና አንድ ጀብዱ ሠርቶ ለንጉሡ (ለአማቹ) ለማሳየትና ለመፎከር ጉጉት እንደሚያድርበት አይጠረጠርም ። ከዚህ በፊት በ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ከግራኝና ከአቡበከር ጋር ተጋጥሞ መሸነፉ ፤ ከአይፈርሱ ጦርነት በሚስቱ በኩል በብልጠት ተላልኮ መለወጡ ይኸ ሁሉ ተሰብስቦ በላዩ ላይ አንድ የኀፍረት

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 281 - 295

ስሜት ስለሚፈጥርበት ይኸን ሁሉ ለማደስ በመመኘት ግራኝ ለጦርነት ዘዴ (ለታ ክቲክ) ሲል የለወጠውን የጦር ግንባር አሸንፎ እንዳባረረ አስመስሎ ራሱ ተታሎ ንጉሡንና በሌላ በር የሚከላከሉትን የጦር አለቆች አታሎ እንዲዘነጉ አደረጋቸው ።

ግራኝ አህመድ እታች ሆኖ የጦርነቱን የሥፍራውን አቀማመጥ እየመረመረ በሚመለከትበት ጊዜ የርሱ ተዋጊዎች ለማጥቂያ ከማይመች ቦታ ላይ ሆነው ከላይ በናዳና በቀስት መጠቃታቸውን ተመልክቶ ተዋጊውን ጦር በቁጣ ከዚያ ያስነሣው በሌላ በኩል በሚመች ቦታ ላይ እየተዋጋ ከሸዋ ድረስ ቁጥሩ የበረከተ ጦር ይዞ የመጣበትን የድል ምኞቱን ለማከናወን እንጂ በዚች በአጉል ቦታ ጦሬ ለማጥቃት ካልተመቸው ወደመጣሁበት ወደሸዋ ልመለስ ለማለት አልነበረም ። በዚህም ራሱ ደገልሃን እንደምን እንደተሳሳተ ንጉሡስ እንደምን ተታለው በዚህ ዝቅተኛ የጦር ክንውን ተማምነው ግብር እስከማብላትና በጣም እስከመደሰት እንደምን እንደደ ረሱ ሊገባን አይችልም ።

ነገር ግን ይህ መሠረት የሌለው ደገልሃን ለመፎከሪያ ጭምር ያመጣው ደስታ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ግራኝ ንጉሡ ባሉበት በዋስል በኩል ሄዶ በነአይበስ ለሐዬ ምክር በከሐዲዎቹ በነአናንያ እየተመራ የሚያደርገው ውጊያ ነገሩን ሁሉ ለዋውጦ ንጉሡንና ጦራቸውን ከአጭር የደስታ ጊዜ በኋላ ከዚያው ከነበሩበት ኀዘ ንና ስደት ሲመልሳቸው እነሆ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን ።

ISIC

## ምዕራፍ ፰

## የዋስል ጦርነት - የንጉሡ መሸነፍና መሸሽ (፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ጥቅምት ፳፱ ቀን)

የግራኝና ያዬ ልብነ ድንግልን የጦርነት ታሪክ በዘመኑ ጦርነቱ የተነሣበትን ምክን ያት የግራኝን ጥብቅ ተዋጊነት የአመራሩን ዘዴ ከቱርክና ከዓረቦች ዘንድ የሚያገ ኘውን እርዳታ ጉዳዩን በየበኩሉ አጥንቶ ከጽሑፍ ላይ አሥፍሮ ለአንባቢ ሕዝብ ሊያቀርበው የቻለ ጸሐፊ ካለመኖሩ የተነሣ ይኸን ታላቅ ጦርነት የተደረገበትን ታሪክ ሕዝብ እንዳለ በዝምታ ውስጥ ሊያልፈው ስለማይችል ከቤተ ክህነትም ከሕ ዝብም የተውጣጣ አንድ የግራኝ ጦርነት ተረታዊ ታሪክ መፍጠር ግዴታ ሆኖ እስ ካሁን ሲባል የቆየውን በምዕራፍ ፳፮ አመልክተናል ። የዘመኑም ጸሐፊዎች የቤተ ክህነት ሰዎች ከመሆናቸው የተነሣ በብሉይና በሐዲስ በዚማና በቅኔ የጠ ለቀ ዕውቀት ሲኖራቸው ወደዚህ ወደ ደንበኛው የታሪክ ዕውቀት የዘመኑንም የውጭ ፖለቲካ በቱርክና በፖርቱጋል መካከል ያለውን ባላንጣነት በዚህ ዘመን ያሉ የአውሮፓ ጸሐፊዎች ላገራቸው ሕዝብ በሚያቀርቡት ታሪካዊ የጽሑፍ ምርት የታሪክን ጽሑፍ ከሌላው በማገናዘብ የአነጋገር ወዝ እየሰጡ ለማቅረብ የተፈጥሮ ዕውቀትና ችሎታ ሳይሆን የዘመኑ ትምህርትና የአጻጻፉ ልምድ ስለሚጐድላቸው እንኳን የአነጋገር ወዝ የተጨመረበት የታሪክ ጽሑፍና ደረቁም ታሪክ በዝርዝር

የተጻፈ ከመጥፋቱ የተነሣ እነሆ የጠላት ወገን የሆነው ዓረብ ፋቂህ የጻፈውን መሠረት ለማድረግ ተገደናል ።

በዚህ ምክንያት የግራኝን ድል አድራጊነት የተከበሩትን ንጉሠ ነገሥት መሸነፍ ሕዝቡም ቤተ ክህነቱም ደንበኛውን ታሪክ ስላጣው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከራሱ እያመነጨ በተረት መልክ እንደ ፈቀደው እየፈጠረ በልዩ ልዩ መንገድ ሲያወራው ኖረ ። ባለፈው እንዳነበብነው ተሸንፎ የማያውቀውን ንጉሠ ነገሥት ለማሸነፍ መቻሉ ንጉሡ ቦካን ጦር አውርድ እያሉ በመጸለይ የገዛ ግንባቸውን በጦር በመውጋት ትምባሆ እየጠጡ አምልኮ ባዕድ ስላበዙ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ባንድ እጁ ቋጥኝ ሊወረውር የሚችል ጦሩ አርባ ክንድ የሚረዝመውን የጥይት በትር የትንኝ ያህል እንኳ የማይቀነቅነውን ግራኝን አሥነሣባቸው ከማለት ላይ ደረሰ ። በቤተ ክህነት ሰዎች ላይ የጨከነበትን አብያተ ክርስቲያናትን ገዳማትን አበክሮ ያቃጠለበትን ምክንያትም አባቱን የደብረ ሊባኖስ ገዳም ካህናት በመቋሚያ ደብድበው ስለገደሉበት ነው የሚሉም ልብ ወለድ ታሪክ ተፈጥሮ እንደ ደንበኛ ታሪክ ሆኖ እስከ መወራት መድረሱ ለማንም ግልጽ ነው ።

ባሁኑ ጊዜ ደግሞ የግራኝ አህመድን የድል አድራጊነት ምክንያት ባለፈው ከዘረዘርነው በቀር አንባቢ ራሱ በየምዕራፉ ላይ በሚገኘው በጦር አመራሩና በዘዴው በጭካኔውና በተንኮሉ የተነሣ ወደ ድል ጉዳና የተራመደበትን ምክንያት እንደሚገነዘበው የታወቀ ነው ።

ISIC

እሁንም የርሱ ሰዎች እርሱ በተለመደው የጦር ስልቱ እስቦ ሲያዝ ግንባር ቀደም የነበሩት ወታደሮች አጉል ቦታ ሆነው ሲዋጉ የጠላቶቹ ወታደሮች ከላይ የተመቸ ቦታ ይዘው ሲጐዱበት ወታደሮቹን በእልህ በርቱ ጠንክሩ ወደፊት ግፉ ወደ ኋላ ያለውን እቀጣለሁ እያለ እንደሞኝ የጦር መሪ አላዋጋም ። ነገር ግን ከዚህ ከመጥፎ ቦታ ተዋጊውን ጦር አስነሥቶ ምክር ያዘ ። ይኸን በመሰለ ጊዜ ከርሱ ጋር ከመዠመሪያ ዠምሮ ከዘመቱት ከአዳሎችና ከሱማሌዎች ይልቅ ውስጥ አወቅ የሆኑት የአገሩ የክርስቲያኖች ሹማምንት መሆናቸውን በትክክል ስለሚረዳው እነርሱን ጠይቆ አይበስ ለሐኄ የተባለው የሰጠውን መልካምና ጠቃሚ ምክር ሰምቶ እንደተቀበለው ባለፈው ምዕራፍ አንብበናል ። አሁን በዚህ ምዕራፍ የምናነበው የዋስል ጦርነት ሊከናወን የቻለው ይህ አይበስ ለሐኄ በሰጠው የጦር መላ መሠረት ነው ።

አይበስ ለሐኄ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በእናቱ በኩል ካኄ ልብነ ድንግል ይዛመዳል ። በመዠመሪያ ጊዜ እስላሞችን በጥብቅ የሚጠላ ነበር ። በብዙ ቦታ ተዋግቶ ከተሸነፈና ተሰፋ ከቆረጠ በኋላ ግን በቀወት ወታደሩን ይዞ ለግራኝ አህመድ የገባ ጊዜ ግራኝ እስላም እንዲሆን ቢያባብለው ወደፊት ታማኝ ሆኜ ከእስላምም ከክርስቲያንም ጋር ብትዋጋ ያንተ ረዳትህ ነኝ ሃይማኖቴን ግን አልለውጥም ብሎ እንገራግሮ እንደነበረና በኋላ ግን ወገኖቹ እኛ ስንሰልም አንተ ከማን በልጠህ ነው እምቢ የምትለው ብለው ስለአስፈራሩት እንደሰለመ ባለፈው አንብበ

ናል (1) ። ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት ታማኝነቱን ለመግለጽ ጥሩ ጥሩ ምክር ለግራኝ ካቀረበና ግራኝም በርሱ ምክር ከተጠቀመ ወዲህ ወደፊት ከዋስል ጦርነት በኋላ ከግራኝ ሠፈር አምልጦ ወደ ንጉሡ ሄዶ ተደባልቋል ። በዚህ ዓይነት ውስጡን በልቡ እየተቆጨ በአንደበቱ የሚያቀርበው ምክር ትክክለኛ ነው ማለት ነው ።

ነገር ግን ይፋት ላይ ከጌታው ከአውራይ ኡስማን ጋር ከሦስት ወር በፊት ወታደሩን አሳድሞ ለግራኝ የገባው አናንያ ከከሐዲነቱ አንድም ቀን ሳያዘነብል ግራኝን እየጠቀመ ወገኑን በጥብቅ እንደጐዳ በዚህም በዋስል ጦርነት መንገድ በመምራት ክርስቲያን መስሎ ወገኖቹን ባላገሮች በአነጋገር እያታለለ እንደምን እንደሚያገለግል ከዋናው የጦርነት ታሪክ ጋር ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ እንደሚከተለው እናንብብ ።

«ይማም ጦሩን ከፋፍሎ ኤሚር ዘሀርቡይን ፤ ፋራቃሃም አሊን ፤ አውራይ ሺሃብን ፤ አውራይ ኡመር ዲንን ፤ ገራድ አህሙሹን ጨምሮ የበላይ መሪ ወዚር ኑርን አድርጎ እናንተ ከኋላ ሆናችሁ ደገልሃን የመጣባችሁ እንደሆነ ተዋጉት እኔ ከፊት ሆኜ እየመራሁ የሀበሻው ንጉሥ ወዳለበት እንጓዛለን ብሎ ነገራቸውና . . . . . . ጉዞው ተዠመረ ። አናንያ እፊት እፊት ይመራ ነበር ። አውራይ ኡስማን ግን ከይማም ጋር ሳይለይ አብሮ ይጓዝ ነበር ። በዚህ ጊዜ ደገልሃንም ያለበትን ሥፍራ ትቶ በመጥፎ መንገድ ወደ ንጉሡ ጉዞውን ዠምሮ ሳይመካከሉ ወንድሙ ሐንታዝ (አንያስ) የእስላሞቹን ከተራራው ሥር መነሣታቸውን ሳያውቅ ወታደሮቹን ይዞ ወደ ደገልሃን ለመሄድ ሲጓዝ በድንገት ከእስላሞቹ ግንባር ቀደም ጦር ከነአናንያ ተገናኘ ። እነአናንያም ክርስቲያኖቹን ከበው ከፈረስና ከበቅሏቸው ጋር ማረኳቸው ። ሐንታዝ ግን ከፈረሱ ወርዶ ጫካ ውስጥ ገብቶ አመለጠ ። አናንያም የማረከውን ሁሉ አምጥቶ ለይማም ቢያቀርብ ይማም ሁሉንም ለአናንያ ጌታ ለአውራይ ኡስማን ተወለት ። እርሱ ደግሞ መልሶ ለአናንያ መርቆ አስደሰተው ።

ከዚያ በኋላ ይማም አህመድ ጎጅማህ ውስጥ አብሸሉ ዘራፍ እሚባለው አገር ላይ ሠፈረ . . . . . . (2) ። ይማም መሪውን አናንያን ጠራና ይህ ዛሬ ያለፍነው ጠባብ መንገድ ምነው እንደዚህ ሆነ ቢለው የነገው ከዛሬው የባሰ ይሆናል ብሎ መለሰለት ፤ ታዲያስ ምን ይሻለናል ቢለውም ጦሩን እሦስት ከፍሎ መጓዝ ነው ብሎ መለሰና በማግሥቱ ከጥበቱ የተነሣ ጦሩ ተቀጣጥሎ ሲጓዝ አንድ ተራራ ይማም አይቶ ይህ የማየው . . . . . . ተራራ ምንድነው ፤ ብሎ አናንያን ቢጠይቀው "ንጉሡ አሁን አለበት የሚባለው የዋስል ተራራ ይህ ነው" ብሎ መለሰለት ። ታዲያ አሁን ንጉሡ በዚያ ይኖር ይሆን ፤ ብሎ ቢጠይቀው እኔ እንዳንተው ወሬውን አብረን ሰማሁ እንጂ በተለይ የማውቀው ነገር የለም ፤ አሁን ግን በፈረስ ሄጄ ወሬ ተጠይቄ አመጣልሃለሁ ብሎ ከአራት ፈረሰኞች ጋር እልፍ እንዳለ የክርስቲያኖቹን እረ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 269 - 270

(2) በባሽሎ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኝ ዘራፍ የሚባል ሠፈር ይኖር ይሆን ? ።

ኞች አገኙዋቸው ። እረኞቹም "ከወዴት መጥታችኋል ?" ብለው እነ አናንያን ሲጠይቋቸው "እኛ የደገልሃን ወታደሮች ነን አለቃችን ደብዳቤ ለንጉሡ አድርሱ ብሎን እንጓዛለን ንጉሡ ያሉበትን ታውቃላችሁ?' አሏቸው ። እረኞቹም "አዎን እናውቃለን ንጉሡ ያሉት በዚህ ተራራ ላይ ሀጉዋ (ሐጓ) እሚባለው ሥፍራ ላይ ነው" ብለው መለሱ ።

ከዚህ በኋላ እስላሞቹ እረኞቹን ይዘው ወደ ይማም አመጧቸው አናንያ ይኸው እነዚህ እረኞች ንጉሡ ያለው በተራራው ላይ ነው ብለውን ይዘን ወደ አንተ አመጣናቸው ብሎ ለይማም ቢነግረው "ለክርስቲያኖቹ ሄደው ወሬ እንዳይነግሩ እነዚህን መግደል ይሻላል" ብሎ ነበር አናንያ ግን እነዚህ እኛ እስላሞች መሆናች ንን በፍጹም የማያውቁ ባላገር ናቸው ይልቅስ የገደልናቸው እንደሆነ የመንደሩ ሕዝብ እዚህ መኖራችንን ያውቅና ወሬውን ለንጉሡ ያደርሳል ስላለ እውነትህ ነው ልቀቃቸው አለው ።

ከዚህ በኋላ ይማምና ጦሩ እረኞቹ ባመለከቱበት አቅጣጫ ይጓዙ ዠመር ። በዚህም ጊዜ ክርስቲያን ሰው እመንገድ ስታገኙ በቋንቋው አነጋግሩት እንጂ እስላም መሆናችሁን ለማንም አትግለጹ ፤ ሰውም ሲጠይቃችሁ የደገልሃን ወታደ ሮች ነን ወደ ንጉሡ እንሄዳለን በሉት ብሎ ለሠራዊቱ አስጠነቀቀ ።

እንደዚህ ሆኖ ጥቂት እንደ ተጓዙ በተራራው ላይ የተተከለውን የንጉሡን ነጭ ድንኳን ተመለከቱ ። ከድንኳኑ ትልቅነት የተነሣ የሁለት ቀን ጕዳና ርቆ ለተ መለከተው ሰው ይታያል ። ርዝማኔው ፳ ክንድ ነው ፤ ቁመቱ ከ፱ ክንድ ይበል ጣል ። እስላሞቹ ይህ የሚታየው የንጉሡ ድንኳን መሆኑን በተረዱ ጊዜ እኋላ ያሉት የክርስቲያን ሰዎች እስኪጠጉ ድረስ እርምጃቸውን ቀንሰው ቀስ እያሉ ይጓዙ ዠመር ሰዎቹም የለበሱት የክርስቲያን ልብስ ነበር ። ይማም "አደራችሁን በእግ ዚአብሔር በራሳቸው ቋንቋ በኤልጅጁ (1) አነጋግሯቸው አለ ። ክርስቲያኖቹም ወደ ሥራቸው የሚጓዙ ነበሩ አጠገባቸው ያሉት እስላሞች መሆናቸውን አላወ ቁም ። እንዲያውም አንዲት ሴትዮ ደገልሃን መስሏት ለይማም አቤቱታ አቀረ በች ። ይማም እሬቱ አቅርቦ በኤልጅጁ ቋንቋ ሊያነጋግራት ፈልጎ ሳለ ዕቃዋን መልሱላት ብሎ በእስላም ቋንቋ ስለተናገረ ንግግሩ ገባትና ቀስ ብላ ወደኋላዋ ተመ ልሳ ተቀምጣ "እነዚህማ እስላሞች ናቸው !" ትል ዠመር ። ነገር ግን እስላሞቹ የርሷን መረዳት ሳያጤኑ ዝም ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

ከነርሱም ጋር የነበሩት ክርስቲያኖች ግማሹ ገበሬ ወደ እርሻው የሚሄድ ግማሹ ልብሱን የሚያጥብ ግማሹ ወደ ንጉሥ ወናግ ሰገድ ዱቄት ጭኖ የሚጓዝ ግማሹ ላቤቱታ የሚወጣ ነበር ። በአጠገባቸው የሚጓዘው የእስላም ጦር መሆኑን ሳይረዱ እስከ ተራራው ጥግ ድረስ አብረው ተጉዘው በመጨረሻ በቀኝ በኩል አድ ርገው ወደ ኩተማዩቱ ወደ ዋስል ደረሱ ። በዚያም ንጉሡም ጦሩም እስላሞቹን አሸንፌ ወደ ፈጠጋር አባረርኋቸው ብሎ ደገልሃን በጻፈው እየተደሰቱ ተቀምጠው

(1) ኤልጅጁ ሲል ምን መሆኑ አይገባንም ፤ የየጁ (አማራ ሳይንት) አማርኛ ማለቱ ይሆን ?

ነበር እንጂ የእስላሞቹን መጠጋት አልጠረጠሩም ።

መሪው አናንያ ወደ ይማም ሄዶ ይኸውና እሥፍራው ደረስን ቢለው አሳብ ህን እስቲ ንገረኝ ብሎ መልሶ ጠየቀው ። አናንያም እንደኔ አሳብ የሆነ እንደሆነ የኋለኛው ጦር ጨርሶ እስኪደርስ እዚሁ ሥፍራ እንደርና ሲነጋ ያለንን መድፍ ከፈ ረሰኞቻችን ፊት አስቀድመን የእግረኛው ጦር ከኋላ ሆኖ ተራራውን ወጥተን እን ወጋቸዋለን እግዚአብሔርም ድሉን ይሰጠናል ብሎ ቢመልስ ይማም ክርስቲያኖቹ እስላም መሆናችንን አውቀዋል ወይስ የደገልሃን ጦር ነው የመሰልናቸው ብሎ እን ደገና ጠየቀው አናንያም የለም የደገልሃን ጦር ነው የመሰልናቸው ብሎ መለሰ እን ግዲያውስ ካላወቁን ለምን እስክንነጋ እንጠብቃለን አሁኑኑ ተራራውን እንውጣ አለ ። አናንያ የእግረኛና የፈረሰኛው ጦር አልደረሰምና ብንጠብቅ አይሻልምን … ቢለው ተራራውን መውጣት ብንዠምር እኋላም ያለው ጦራችን ይደርሳል እዚህ ያደርን እንደሆነ ሌሊቱን ክርስቲያኖቹ ይሰሙና መውጫ መንገዳችንን ይይዙብ ናል ከዚያም አንድ ሰው ብቻውን ከላይ የድንጋይ ናዳ ቢለቅብን ከኛ መድፍ የበ ለጠ ጉዳት ሊያደርግብን ይችላል ። ስለዚህ አሁን እንውጣ ብሎ ይማም ለመው ጣት መቁረጡን ሲመለከት አናንያ እንግዲህ እኔ የምሰጠው አሳብ የለም ትእዛዝ መስጠት ያንተ ፋንታ ነው ብሎ መለሰለት ።

በዚህ መካከል ኤሚር አቡበከርና በለው አብዶ ጌታ ሆይ አናንያ እውነቱ ነው ብለው ቢናገሩ ይማም ለነሱ ምንም ሳይመልስ ወደ አብሳማ ኑር ፊቱን አዙሮ ደገልሃን በያዘው ተራራ በኩል እንውጣ ብትለኝ አይሆንም ከርሱ የተሻለ አለ ብዩህ የነበረው ይኸውልህ አለው አብሳማ ኑሮም እውነትህ ነው እንውጣና ብንሞ ትም እንሙት ብሎ መለሰለት ።

ከዚህ በኋላ ይማም እፈረሱ ላይ ወጣና "መሣሪያችሁን ያዙ እግዚአብሔር ይባርካችሁ" ብሎ ተናገረና ሁሉም የጦር ልብሱን መልበስና መሣሪያውን መያዝ ዠመረ ፣ ከነዚህም ውስጥ የነበሩት ዋነኞቹ አብሳማ ኑር ፣ ኤሚር ሙጃሂድ ፣ ኤሚር አቡበከር ቀጢን ፣ አህመድ ጎይታ ፣ አደሙሽ ፣ አውራይ አቡበከር ፣ አሊ ኤሚር አቡበከር ቀጢን ፣ አህመድ ጎይታ ፣ በለው አብዶ ፣ አሊ ታይ ኢጅር ፣ አውራይ ኡስማን ቢንዳር አሊ ፣ ያኪም ፣ ጎይታ ፣ በለው አብዶ ፣ አሊ ታይ ኢጅር ፣ አውራይ ኡስማን ቢንዳር አሊ ፣ ያኪም ፣ አዝማች ሃይቤ ፣ ፈራቃሃም ሶልጣንና ኢሳ ነበሩ ። ይማም ሳክብ እሚባለው ፈረሱ ላይ እንደሆነ የእግረኛውን ጦር አዛዥ አስጠራና እግረኛው እሁለት ተከፍሎ አንዱ ክፍል በዛፉ ውስጥ በተራራው ጐን መውጣት ይዠምር ፣ እኛ የመካከለኛ ውን መንገድ ይዘን ስንወጣ ድንገት እመንገድ ላይ ክርስቲያኖች ተገኝተው መተላ ለፊያ የዘጉብን እንደሆነ ይዋጉ ብሎ ለ፪ኛው ክፍል በፊንጅ ሳባር ለሚታዘዘው ጦር በፈረሰኞቻችን ፊት ለፊት ቀድማችሁ ተጓዙ ብሎ አዘዘ ። ወታደሩም ሰይፉን መዞ በእጁ እንደያዘ ጋሻውን እንዳነገበ ጉዞው ተዠመረና . . . . . . ተራራውን መውጣት ዠመሩ ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ በተራራው ያለው የክርስቲያን ጦር የእስላሞቹን በቅርብ መኖር አላወቀም ነበር ። ይማም ከነጦሩ ግማሽ መንገድ እንደተጓዘ አንድ በጫት የሰከረ እተራራው ሥር የነበረ እስላም አጠገቡ አንዲት ቤት ክርስቲያን አቃጠለ ።

ክርስቲያኖቹ ከላይ ከተራራ ቁልቁል ቃጠሎውን ተመልክተው ተሸበሩ ። እስላሞቹም ወደኋላቸው ዘወር ቢሉ ቃጠሎውን አዩ ። ይማምም አብሮ አየና ይኸን ያደረገው ሰው እግዚአብሔር የረገመው ነው ብሎ ጮኸና ወዲያው ክርስቲያኖቹ ይኸን ቃጠሎ ዓይተው ሳይሸሹ ፈረሳችሁን ባለንጋ እየመታችሁ በችኩላ ውጡ ብሎ ፈረሰኞቹን አዘዘ ።

ክርስቲያኖቹም በበኩላቸው ግማሾቹ ፈረሶቻቸውን ሲጭኑ ግማሹ ጦርና ጋሻውን ሲያዘጋጅ አፈት ቀድመው የነበሩት እነ አብሳማ ኑር የፈረሶቻቸውን ልጓም ለቀው እየጋለቡ "አላህ ታላቅ ነው" ብለው ጮኸው እመካከላቸው ገብተው ይዋጉ ዠመር ። ወደ ጦሩ ቀድሞ የገባው አዳሙሽ ካንድ ክርስቲያን ጋር ተጋጥሞ በጦር ገደለው ። አብሳማ ኑር ግን እተዋጊው ወታደር መካከል ሆኖ "ከአምላካችን ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም መሐመድም የእግዚአብሔር ሐዋርያ (መላክተኛ) ነው" እያለ እየመላለሰ ይጮህ ነበር ። ከክርስቲያኖቹ ግማሾቹ ወደ ንጉሡ ድንኳን እየሮጡ ሄደው ተሰበሰቡ ፤ ግማሾቹ ወደ አገኙበት ሥፍራ ወደ ፊታቸው ሸሹ ። ንጉሡም ከድንኳኑ ወጥቶ እፈረሱ ላይ ወጣ ፩፻ የሚሆኑ ፈረሰኞችም በዙሪያው ሆነው ወደ ርሱ ሰው እንዳይቀርብ ይከላከሉ ነበር ። እግረኛውም ጦር ብዙ ነው ።

ክርስቲያኖቹ በንጉሡ ዙሪያ የተሰበሰቡ ጊዜ እስላሞቹ ይማም አህመድ እስኪደርስ ድረስ ይጠብቁ ነበር ። ይማም ግን በንጉሡ ድንኳን ዙሪያ የተሰበሰበውን የጦር መጠን ሲመለከት ኃይለኞቹ ፈረሰኞች እነአብድ ኢን ናስር እነሰበር ዲን .... ከኋላው ደረሱለት ፤ እንደዚህ ሆነው እስላሞቹም ክርስቲያኖቹም በየሥፍራቸው ቆመው ሳሉ ከክርስቲያኖቹ መካከል አንዱ ተነጥሎ ፈረሱን እስነሥቶ እየጋለበ ወደ እስላሞቹ መጣ ሳብር ኤድ ዲን ጦሩን ገትሮ ሊዋጋው ወደ ርሱ ሲጋልብ ያኛው "ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም መሐመድም የእግዚአብሔር መላክተኛ ነው" ሲል ሰማውና ነገሩ ገርሞት ሳይወጋው ተመለሰ ያኛው እይማም ፊት ቀረበና ምንድነህ ? ብሎ ቢጠይቀው እኔ ጀሹ (ጎሹ) እባላለሁ የማምነው በአላህና በነቢዩ በመሐመድ ነው ፤ ልጄ በሸራህ ከናንተ ጋር አብሮ አለ ብሎ መለሰ ። ይማም እግዚአብሔር ታላቅ ነው እስላም ነውና ልቀቁት ብሎ ተለቀቀ ።

ISIC

ከዚያ ቀጥሎ እንግዲህ እዚህ ምን እቆየን ሄደን እንዋጋ ተባብለው ...... እየተሽቀዳደሙ እክርስቲያኖቹ መካከል ገብተው ይዋጉ ዠመር ፤ አንድ ሰዓት ያህል እንደተዋጉ እግዚአብሔር በክርስቲያኖቹ ልብ ፍርሃት አስገብቶ ሽሽትን ጀመሩ ፤ እስላሞቹም ሁጉዋ (ሐን) እስከሚባለው ተራራ ድረስ እየተከታተሉ መቱዋቸው እሸሹበትም ተራራ ድረስ እያባረሩ በሚዋጉበት ጊዜ አው እቡበከር ፋኪር ......የሚባለው አንድ የንጉሡን ባለሟል አግኝቶ መትቶ ከፈረስ ላይ ገልብጦ ጣለውና "አንተ ንጉሡ አይደለህምን" ብሎ ይዞ ቢጠይቀው "የለም እኔ አይደለሁም ንጉሡ ያውና" ብሎ በጣቱ አመለከተ ። እቡበከር ግን የለም ስታታልለኝ ነው እያለ ከርሱ ሲነጋገር የክርስቲያኑ አሽከሮች ሮጠው መጡና ግማሾቹ ፈረሱን ግማሾቹ እርሱን ደብድበው ማረኩት ። ይማም እርሱን ለማስጣል ወደነርሱ

ገሥግሦ ተዋግቶ አስጣለው ፤ በዚያን ጊዜ የሀበሻው ንጉሥ ይማምን ግራኝ ስለነበረ ጐራዴውን በግራ እጁ እንደያዘ አየውና በፈረሱ ምልክትና በግራኝነቱ አውቆት "ያውና በሰው አምሳል የተመሰለው ሰይጣን" ብሎ አጠገቡ ላሉት ጓደኞቹ ተና ገረ ። ወታደሮቹም በመተትህ (በጥንቆላህ) ያዝኸን እያሉ ጮኹ ። ይኸንንም ማለ ታቸው ይማምን የማፍዘዣ ዕንጨት (ከዛፍ) እየቆረጠ በዚያ እየተዋጋ በአስማት ያሸንፋል ማለታቸው ነው ። ነገር ግን ይዋሻሉ ።

ይማም እመካከላቸው ገብቶ በብርታት ተዋግቶ በታተናቸው እነርሱም ወደ ተራራው ለመሸሽ ከፈረሳቸው ወርደው ልባቡን እየሳቡ በግራቸው ተራራውን ለመውጣት መንገድ ሲፈልጉ ይማም ከኋላችሁ እንደርስባችኋለንና ፈረሳችሁን ለቃችሁ ሽሹ ብሎ ጮኸባቸው እነርሱም ይኸንን ድምፅ ሰምተው በፍርሃት በጉል በታቸው ጭምር እየዳሁ በጣር ወደ ተራራው ወጡ ። እንዳንዱም እዛፍ ላይ ወጥቶ ለመደበቅ ሲሞክር ቅርንጫፉ እየተሰበረበት እስላሞቹ መካከል እየወደቀ አግኝ ተው ገደሉት ። ይማም የክርስቲያኖቹ ፈረሶች የሚያማምር ኮርቻና ቀያይ ግላስ እንደ ተጫኑ ወደቆሙበት ሰው ልኮ አስወሰዳቸው ቊጥራቸው ፸ ይሆናል ። ከይ ማም ጋር ያሉት አብሳማ ኑር ፤ ያኪም አዳሙሽ ፤ ኤሚር ሙጃሂድ ፤ ገራድ አህማ ዱሽ ፤ ፋራቃሃም ሳቱ ፤ አብደላ ቤን ሞሀራም የማህራው (ዓረቡ) ነበሩ እነዚህም በየበኩላቸው እየተዋጉ ሲገድሉ ሲማርኩ ነበር ።

በዚህ ጊዜ የሀበሻው ንጉሥ ከፈረሱ ወርዶ ፲፭፻፳ እፊቱ አራት የተጫኑ ፈረሶ ቹን እያሳበ ከመንገዱ መጥፎነት የተነሣ ወደፊት በእግሩ ሲጓዝ ይማም በበኩሉ እንደዚሁ በሌላ መንገድ በእግሩ ሄደ ። ሌሎቹ እስላሞች እነገራድ ኡስማን እነአ ውራይ ኡስማን በመንገድ ንጉሡን ቀድመው አለፉ ። ንጉሡም እነሱን ባየ ጊዜ እነሱ ሳያዩት አጠገቡ አለው ዛፍ ውስጥ ገብቶ ተደበቀ ። ይማምና ጓደኞቹም ንጉሡ ካለበት በታች ቀደም ብለው ደረሱ . . . . . . አንድ የክርስቲያን ፈረሰኛ እየ ሮጠ ሲመጣባቸው አውራይ ኡስማን ገጠመውና ማረከው ይኸም ሰው በንጉሡ ዘንድ የተከበረ ትልቅ ሰው መሆኑ ሲታወቅ በይማም ትእዛዝ ተገደለ . . . . . እስላ ሞቹ በዚሁ ቦታ (ንጉሡ ባለበት) እንዳሉ ወዲያው ዝምበር ጠለቀች ደመናም ሆነ ዝናብም ይዘንም ዠመር ኃይለኛ ብርድም ተነሣ ። በዚህ ጊዜ እስላሞቹ ወደ ጓደኛ ቻቸው ወደ ሠፈር ተመለሱ ። እነሱም ሲመለሱ ንጉሡ ከነበረበት ሥፍራ (ጫካ) ወጥቶ በአምባ (አምባ ግሺን) መንገድ አድርጎ ሊሊቱን ሁሉ ሲጓዝ አደረ ።

እስላሞቹ ወደ ሠፈር ሲመለሱ ጓደኞቻቸው እሳት አንድደው አገኙአቸው ከዚያ በደስታ ወደ የክርስቲያኖቹ ድንኳን ገቡ ። ድንኳኑ ሁሉ በወርቅ በብር በፈ ረስ በበቅሎ በቤተ መንግሥት የሐር ልብስ ተመልቶ ነበር ። ከሐሩም ልብስ ውስጥ በወርቅ የተጠለፈ ግማሹ የንጉሡ ፤ የቀረው የቤተ ሰቡ ነበር ። ከዚሁ ጋር በሺ የሚ ቆጠሩ ቆነጃጅት ሴቶች የሹማምንት ወንድና ሴት ልጆች አብረው ተገኙ ። የን ጉሡ ድንኳን በውስጡ ዙፋኑና መሣሪያው እንዳለ እንደተተከለ ተገኘ ። ይማም ከጓደኞቹ ጋር በተገናኘ ጊዜ ስለአገኘው ድል አምላኩን አመሰገነና በንጉሡ ድን ኳን የተገኘውን ምን አደረጋችሁት ብሎ ቢጠይቅ የጦር መሣሪያ የሆነውን እስላ

ሞቹ ተከፋፈሉት ዙፋኑና የሐር ልብሱ በውስጡ እንዳለ ነው ብለው መለሱለት ከዚያ ድንኳኑ አያስፈልገኝምና ቅደዱት የሐሩን ልብስና ዙፋኑን ግን አምጡልኝ ብሏቸው እነሱም ሄደው ድንኳኑን በሰይፋቸው ቀዳደው ጣሉት ።

እስላሞቹ ሌሊቱን ሁሉ በደስታ አደሩ ከጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ በገራድ አህሙሽ የሚታዘዘው የመካከለኛው ያንድ ክፍል ጦር ደርሶ ተራራውን በሚወጣበት ጊዜ ይማም ድዙኤል ድኛህ ብሎ የሠየመው የአህሙሹ ፈረስ አድጦት ወድቆ ተሰ በረና እዚሁ እሠፈር ሞተ ። አህሙሹም ስለፈረሱ ቢያለቅስ ይማም ከተማረኩት ከንጉሡ ፈረሶች የሚያምረውን ፈረስ ተካው ። ደጀን የነበሩት ወታደሮች ጦርነት አልተካፈሉም ። ጦርነቱ የሆነለት እመንገድ አድረው በማግሥቱ ደረሱ ። እነሱም ሲደርሱ ከየጓደኞቻቸው ጋር ተገናኝተው ሰላምታ እየተሰጣጡ ስለተገኘውም ድል እግዚአብሔርን አመሰገኑ ። ይማም በውጊያውለት ሳትደርሱ ቀርታችሁ ምንም አላገኛችሁም ብሎ ለየእንዳንዳቸው አንዳንድ ፈረስ አደላቸው ።

የዋስል ጦርነት ዓርብ ለት በ፲፮ ረቢ ፱፻፴፰ በሂጅራ ቍጥር ተፈጸመ» ሲል ዓረብ ፋቂህ የዋስልን ጦርነት እዚህ ላይ ያቆማል (1) ።

በዚህ ምዕራፍ ላይ የግራኝ አህመድን የጦር ስልትና ተንኮል በሰፊው በምንመለከትበት ጊዜ ወንጌሉ እንዳለው ያገርና የወገን ጠላት ያው ወገን መሆኑን በአንያ እንመለከታለን ። በዚህ መካከል የዓረቡ ጸሐፊ የሚለው ትክክል እንደሆነ ጸሐፊውንም አንባቢውም በጣም የሚገርመው ባዬ ልብነ ድንግልና በሹማምንቶቻቸው በኩል የሚታየው የቆየው ቸልተኝነትና ሥንፍና አሁንም መቀጠሉ ነው ። ለዘዴ (ታክቲክ) ሲል አህመድ ያቋረጠውን የማያትን ውጊያ ተሸንፎ እንደሸሸ አስመስሎ ደገልሃን ባወራው እንደ ትልቅ ድል አድርገው በመደሰት በጥብቅ ሊጠበቅ የሚገባውን በር ችላ ብለው ግራኝ ከነጦሩ ካገር ተወላጅ ገበሬና ነጋዴ ገበያተኛ ጋር ረኸርም ጉዞ ተጉዞ አጠገባቸው እስኪደርስ እንደምን ዝም አሉት ? በዚህ አስፈሪና አደገኛ ጊዜ ተንኮለኛው ግራኝ የማያትን በር የለቀቀው ምናልባት በዚህኛው ለመምጣት ይሆናልና በየሥፍራው ጠባቂ ይደረግበት የሚል ከዚያ ሁሉ ሹማምንት ከዚያ ሁሉ አዋቂ እንዴት ጠፋ ? ባለፉት ጦርነቶች ይህን የመሳሰሉ ስሕተቶች ተደርገው በነዚያም ስሕተቶች ግራኝ ተጠቅሞባቸው ሳለ ያለፉት ስሕተቶች ባሁኑ ጊዜ እንደምን ለትምህርት ሳይሆኑ ቀሩ ? ግራኝ ከነጦሩ ችላ የሚባል ነው እንዳይባል ንጉሡን በጦር አሸንፎ የደቡብ ግዛታቸውን ሁሉ አስለቅቆ እስከዚህ እስከ ዋስል ድረስ ለማባረር የቻለ ያን ሁሉ ታላላቅ መኳንንት ያስፈጀና የፈጀ መሆኑ ከታወቀ አምስት ዓመት አልፎታል ።

በያዘው ስፊ አገር ከዚህ በፊት ባገኘው ድል ተደስቶ ይመለሳል ወይም በዚያው ረግቶ ይቀመጣል ተብሎ እንዳይገመት እርሱ ራሱ አስቀድሞ ለራስ ወሰንሰገድ በጻፈው ደብዳቤ ገልጾት የነበረውን በቅርብ ጊዜ ለራሳቸው ለንጉሡ በጻፈላቸው ደብዳቤ ውስጥ "እንደ ቀድሞው አንድ ጊዜ ባገር ገብተን ወደ አገራችን ተመ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 295 - 306

ልሰን የምንሄድ አይምሰልህ አገሪቱን በሙሉ ድል አድርገን እስክንገዛ ድረስ እን መለስም” ሲል በግልጽ አረጋግጧል ። ጊዜው ክረምት ስለሆነ በክረምቱ ወራት ወደዚህ ሊመጣ አይችልም ተብሎም እንደሆነ ራስ ወሰን ሰገድን ተከታትሎ ከቦ ሰት ተራራ ሳይደርስ ተዋግቶ ያስገደለው በዋናው የክረምት ወር መሆኑን አይስቱ ትም ።

እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ያው በጫት የሰከረው እስላም እተራራው አጠገብ ያገኘውን ቤተ ክርስቲያን ባያቃጥልና በርሱ ቃጠሎ ክርስቲያኖቹ ባይነቁ ኖሮ ከቅምጣቸው ሳይነሡ እስላሞቹ በቀላሉ ንጉሡን ጭምር ሊማርኩዋቸው ይችሉ ነበር ማለት ነው ።

ስለዚህ ንጉሡ በስንፍናቸው ራሳቸውን ከመጉዳታቸው በቀር እግዚአብሔር በወገኖቻቸው በነአናንያ ከዳት የጐዳቸውን ያህል ላሁኑ ሽሽት በጠላታቼው በአ ቃባዩ እስላም መልሶ ጠቅሟቸዋል ማለት ነው ። ነገር ግን እርሳቸው ሊከተሉት ይገባው የነበረውን የርሱን ንቃትና ትጋት ድፍረቱንና ዘዴውን ወደሌላ ትርጉም ለውጠው ግራኝ እርሳቸው ወዳሉበት ተጠግቶ በኃይል ሲዋጋ ባዩት ጊዜ “በሰው የተመሰለው ሰይጣን ያውና” ብለው ተናገሩ ። ሕዝቡም መኳንንቱም በእርሱና በጭፍሮቹ በነ አቡበከር ቀጢን እቅዋም በድፍረትና በዘዴ ሽንጣቸውን ገትረው ውጊያውን በውጊያ ተንኰሉን በተንኰል በመመከት ፈንታ ጉዳዩን ወደ ጥንቆላ ወደ አስማት እየወሰዱ “የማፍዘዣ እንጨት እየቆረጠ በዚያ እየተማታ በአስማት አሸነፈን” እስከማለት መድረሳቸው ሁሉ አሳዛኝም አስገራሚም ነው ። ያ፡ህ ባይ ሆን ኖሮ እኛ ዝግኖቹ መቸ እንሸነፍ ኖሯል በማለት ሥንፍናን የተንተራሰ ከንቱ ሰበብ መሆኑ አያጠራጥርም ።

በግራኝ ጥብቅ ትእዛዝ ከነአናንያ በየመንገዱ ከሚያገኙት ሰው ጋር የራስ ደገልሃን ጭፍራና አጃቢ መስለው በሚጓዙበት ጊዜ በነርሱ በኤልጅጁ ቋንቋ ተን ጋገሩ እንጂ በራሳችሁ (በአዳልኛ ወይም በአዴሬኛ ወይም በዓረብኛ) ቋንቋ አትና ገሩ ብሎ ማስጠንቀቁ ከመንገደኞቹ ውስጥ አንዱ ሄዶ የነርሱን የመጠጋት ወሬ ለክ ርስቲያኖቹ እንዳያደርስ ነው ። በዚህም ላይ እነዚያን በአናንያ በኩል ንጉሡ ያሉ በትን መጥተው ለግራኝ የነገሩት ባላገሮች ግራኝ ወሬያቸውን ከሰማ በኋላ ከእንግ ዲህ ወዲያ እነዚህን መግደል ብቻ ነው ማለቱ ምንም ዓይነት ርኅራኄ የሌለው ጨካኝና የድል አድራጊነቱንና የገዥነቱን ጥቅም ብቻ የሚከተል ነው ማለት ነው ። በውነቱ ይኸን ሰፊ የድል አድራጊነት ዓላማ ለመፈጸም የተነሣ ሁሉ ማድ ረግ ያለበት ይኸንኑ የጭካኔ ተግባር እንጂ ርኅራኄ አይደለም ።

ግራኝ የኤልጅጁ ቋንቋ የሚለው ምን ቋንቋ መሆኑ በትክክል አይገባንም ። ዓረብ ፋቂህም ሙሴ ረኔ ባሴትም ስለአልገባቸው አልገለጹትም ። ኤልጅጁ የሚ ለው በዚያው በቤተ አምሐራ የሚገኘውን የዛሬውን የጁን ይሆን ? የየጁ ቋንቋ ማለቱም የአማርኛ ቋንቋ ማለቱ ይሆን ? አይታወቅም ።

የሆነ ሆኖ በዚህ በሚያሳዝንና በሚያስገርም ቸልተኝነት እንዳሉ ታታሪውና ጥንቁቁ ፤ ጨካኙና ተንኮለኛው ግራኝ ከነጦሩ በድንገት ሲደርስባቸው ካለማወ

ቅና ካለመጠንቀቅ የተነሣ ድንገተኛ በሆነው ጦርነት መሸነፍና መሸሽ ሳይበቃ ቀርቶ ዙፋናቸው ፡ ፈረሶቻቸው ፡ ልብስና መጣሪያው የወርቁና የብሩ ሀብት እንዳለ ከብዙ ቤተሰብ ጋር በእስላሞቹ እጅ በሚያሳዝን አኳኋን ተማረከ ። በውነትም እንደዚህ ያለው ቸልተኝነትና ግዴለሽነት የከበበው ጦርና ሹማምንት ከመሸነፍና እየተዝረከረከ ከመሸሽ በቀር ሌላ ምን እድል ሊኖረው ይችላል ። በዚህ በጦርነት ሰዓት በክርስቲያኖቹ በኩል የሚታየው ጉድለት ሁሉ ባለፈው በሰላሙ ጊዜ የነበረውን የአስተዳደርና የድርጅት ጉድለት በሰፊው ያሳያል ።

ከእንግዲህ ወዲያ ንጉሡ ከዋስል የበሸሎን ወንዝ ተሻግረው ከሸሹ ወዲያ የእስላሞቹ የጦር አለቆች ጭፍራ ጭፍራቸውን እየያዙ በያለበት እየተበታተኑ ስመ ጥር የሆኑትን እነዚያን ከዚህ በፊት ያነሣናቸውን የመካነ ሥላሴን የአትሮንሰ ማርያምን የደብረ ነጐድጓድን የቤተ ሰማያትን የገነተ ጊዮርጊስን አብያተ ክርስቲያናት ሀብታቸውን በመዝመሪያ እየዘረፉ እንደሚያቃጥሏቸው ወደፊት በሚተሉት ምዕራፎች በሰፊው እንመለከታለን ።

በተረፈ በዚህ ምዕራፍ ባለው ታሪክ ውስጥ የምንረዳው እስላሞቹ ይማም አህመድ የሚሉት እኛ ግራኝ አህመድ የምንለው በርግጥ ግራኝ እንደነበረ መጣሪያውን ይጨብጥም ይዋጋም የነበረው በግራ እጁ መሆኑ እነሆ በዓረብኛው በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ በደንብ ተረጋግጧል ። የርሱም አነጋገር በግዕዝኛ በአጭሩ ከተጻፈው ካገራችን ታሪክ ጋር ይገጥማል ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ፡ «ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ በ፲ኛው ዓመት ግራኝ ተብሎ የተሰየመው የኢብራሂም ልጅ አህመድ ከሸምብራ ኩሬ ወጣ (መጣ) ግራኝ መባሉም ግራ እጁ እንደ ቀኝ እጁ ስለ ሆነ ነው» (1) ።

ይህ የዋስል ጦርነት የተደረገበት ቀን ወርና ዓመት በራሱ አጻጻፍ ውስጥ እንዳነበብነው ዓረብ ፋቂህ በ፲፰ ረቢ ፱፻፴፰ በሂጅራ ቊጥር ተፈጸመ ያለውን መጽሐፉን ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት ሊቁ ሙሴ ረኔ ባሴት እንደ ኤው. ቊ ፳፰ (OCTOBER)፲፭፻፴፩ አድርገውታል ።የኛም ታሪክ ነገሥት ዓመተ ምሕረቱን አልጠቀሰም እንጂ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው "ከዚህ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ንጉሡ ወደ አማራ አገር ሄዶ በሐን ተቀመጠ" ካለ በኋላ ከዚያም በጥቅምት ፳፱ ቀን ተሰዶ ሄደ" ብሏልና ቀኑና ዓመተ ምሕረቱ ተጋጥሟል (2) ።

ስለዚህ የዋስል ጦርነትና የርሳቸው ከዚያ ሽሽት የተፈጸመው እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. በጥቅምት ፳፱ ቀን መሆኑ ነው ። ከፈረንጁ ቊጥር ላይ ፯ ቀን ቀንሰው ሲያመዛዝኑት ግን ጥቅምት ፳፩ ይሆናል ።

(1) ወእምድኅረ ኮነ ዝንቱ ኵሉ በ፲ ዓመት ወጽአ እምሸምብራ ኩሬ ውእቱ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ዘተሰምየ ግራኝ በእንተ ዘኮነት እዴሁ ፀጋማዊት ከመ እድ የማናዊት ። ያኄ ልብነ ድንግል ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 11

(2) ወእምዝ በ፪ ዓመት ኀለፈ ንጉሥ ምድረ አምሐራ ወነበረ በሐን ፡ ወእመጽወ፱ቱ ለጥቅምት ተሰደ እምሕየ ። ታሪክ ነገሥት ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 328

ISIC

እንግዲህ ግራኝ በደዋሮ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. አቡበከር ቀጢንን ይዞ ከራስ ደገልሃን ጋር በመዠመሪያ ካደረገው ጦርነት ዠምሮ እስካሁን እስከ ዋሰል ጦርነት እስከ ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ደንበኛው የግራኝ ጦርነት ከተዠመረ ፯ኛውን ዓመት ዠመረ ማለት ነው ። ከሙሉ ሥልጣን ሳይደርስ ከነፋኑኤል ጋር በ፲፭፻፲፮ ዓ. ም. የተዋጋው የተቆጠረ እንደሆነ ወደ ስምንት ዓመት ይደርሳል ።የግራኝም ዕድሜ በዚህ በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. ፳፮ ዓመት ይሆናል ። በ፲፭፻፲፱ ዓ.ም. ዕድሜው ፳፩ ዓመት መሆኑን ከዚህ በፊት ዓረብ ፋቂህ እንዳመለከተ እናስታውሳለን ።

የ፳፮ ዓመቱ ወጣት ግራኝ አህመድ ከሽምብራ ኩሬውና ከዝሆን ዱሩ ጦርነት ወዲህ ፫ኛ ይኸን የዋሰልን ድል አድራጊነት በንጉሡ ላይ ካገኘና ንጉሡ ወደ አምባ ግሼን አቅጣጫ ከሸሹ በኋላ አላይ እንዳልነው በዚህ መካነ ሥላሴ በሚገኝበት ወረዳ ያለውን ስመ ጥር የሆነውን መቅደስ ሁሉ በየአቅጣጫቸው አለቃና ጭፍራ በመላክ ሀብቱን በቅድሚያ እያስዘረፈ አቃጠለው ።

ስለዚህ ከሁሉ በፊት ስለ አብያተ ክርስቲያኑ አተካከል በሚቀጥለው ምዕራፍ ካነበብን በኋላ ከዚያ በሚከተለው ምዕራፍ ደግሞ የነዚህኑ አብያተ ክርስቲያን ዘረፋቸውንና ቃጠሎቻቸውን እናነባለን ።

ISIC

## ምዕራፍ ፳፩

## በቤተ አምሐራ ያሉት የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች

በዚህ በመካከለኛው ዘመን የነበረውና አሁን በ፳ኛው መቶ ዓመት ያለው የባለሥልጣንና የሕዝብ ዝንባሌ በጣም የተለያየ ነው ። በዛሬው ጊዜ በተለይ በአውሮፓ ንጉሥም ቢሆን ፕሬዚዳንት ማናቸውም መሪ ሥልጣን ሲጨብጥ የሕዝቡን ፍላጐት ለማርካት በመንግሥቱ ሀብት አንዳንድ ጊዜም በግሉ ለሕዝብ የሚያሠራው የትምህርት ቤት ሆስፒታል መንገድና ድልድይ ነው ። በሰለጠነውና ነፃነት በተስፋፋበት አገር የሚገኘውም ባለሥልጣን ሥልጣኑን የሚያረጋግጠው ይኸንኑ መልካም ማኅበራዊ ሥራ በፕሮግራም ለሕዝብ ከገለጠ በኋላ ነው ። ክርስትና ከተስፋፋ ዠምሮ እስከ ፲፮ኛው መቶ ዓመት ድረስ ግን እንኳን ከሥልጣኔ ራቅ ብላ የምትገኘው የኢትዮጵያ ንጉሥ የሠለጠኑት የአውሮፓ ነገሥታት እንኳን በየከተማቸው ዋና ዓላማቸው በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ነበር ለዚህም የመንግሥቱንና የራሳቸውን ከፍ ያለ ሀብት ይሠዉት ነበር ።

በዚህ ምክንያት ዛሬ የአውሮፓን ከተሞች የሚጐበኝ በሮማ የቅዱስ ጴጥሮስን ፤ በሎንዶን የቅዱስ ጳውሎስን ፤ በቪዬና የቅዱስ እስጢፋኖስን በመስኮብ የብሥራትን በጀርመን አገር የኮሎኝን በፈረንሳዊ አገር የሻርትርን የአብያተ ክርስቲያን ሕንፃ ውጭውንና ውስጡን ሲመለከት በምን አኳኋን እነዚህ ሁሉ እንደተሠሩ እየተደነቀ በዚያ ዘመን ለዚህ ሥራ ነገሥታቱ የነበራቸውን የጋለ መንፈሳዊ ዝን

ባሌ የአሠሪውንና የሠራተኛውን ድካም የመሐንዲሱን የጥበብ ሙያ በትክክል ይረዳዋል ። የዚህም መንፈስ የመነጨው ከክርስትና በፊት የነበሩት አረማውያን ነገሥታት ለጣዖታቱ ካሠሩት ቤተ መቅደስ ነው ። የነዚያም እንደነዚሁ የተደነቀ እንደነበረ የግብፁን ፒራሚድና የአቴናን አክሮፖሊስ በሩቅ ምሥራቅ በካምቦዲያ የአንኮርን ሕንፃ መመልከት በቂ ነው ።

በዚሁ መንፈስ የኢትዮጵያ ነገሥታትም በአክሱም በላስታ የነበሩት ሁሉ በዘመናቸው አስደናቂ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ሲያሠሩ መኖራቸው ግልጽ ነው ። አንዳንዶቹ በዘመን ርዝመት በፈላሻዪቱ ጦርነት ቢፈርሱ ከዚህ ሁሉ ድነው እየታደሱም ከመሠረት ሕንፃቸውንም ይዘው ወደ ጊዜያችን የደረሱ አሉባቸው ። ጦርነትም እሳትም ሊያፈርሳቸው የማይችሉት ከቋጥኝ የተሠሩት የላሊበላ ሕንፃዎች እነሆ ከግራኝ ቃጠሎና ብዝበዛ በደንጊያነታቸው ምክንያት ብቻ አምልጠው እስከ ጊዜያችን ደርሰው በዛሬው ጊዜ አገር ጐብኝን ከሚስቡት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች ዓይነተኞች ሆነዋል ።

ከዚሁ ተያይዞ ከይኩኖ አምላክ ገምሮ እስከዚሁ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ በሁለት መቶ ሰባ ዓመት መካከል በኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን የተቀመጡት ነገሥታት በየአውራጃው በየተራራው በየደሴቱ ያሠሩዋቸው በጉልትና በሀብት ያደረጁዋቸው መቅደሶች አለቆቻቸውን በወግ በማዕርግ ያከበሩዋቸው ብዙ ናቸው ። እነርሱም እነሆ በአሁኑ ሰዓት የክርስቲያን ጠላት የሆነው ግራኝ እየዘረፈ ያቃጥላቸዋል ። ነገሥታቱም መሣፍንቱና መኳንንቱም መንፈሳዊ ቅናትና ፉክክር ባለበት መንፈስ ገዳም ሲገድሙ ቤተ ክርስቲያን ሲተክሉ አብዛኛውን ጊዜ ምርጫቸው የትውልድ አገራችን ነው በሚሉት አውራጃ ነው ። ብዙም ጊዜ መሣፍንትና መኳንንት ባይወለዱበትም በሹመት በቆዩበት አውራጃ ቤተ ክርስቲያን ተክለው በዙሪያው ከሚገኘው ጉልታቸው ለቤተ ክርስቲያኑ መተዳደሪያ ይሰጣሉ ።

ንግሥት እሌኒ ያዔ በእደ ማርያም ባለቤት ጐጃምን ብዙ ጊዜ ገዝተው የመርጡለ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሲተክሉ የጐጃም ተወላጅነት ያላቸው አይመስለኝም ። ባንድ ወገን ይኖራቸውም እንደሆን አላረጋግጥም ። አባት ግን የደዋሮው ባላባት መሐመድ መሆኑ በየመጽሐፉ ተመልክቶ ይገኛል (1) ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት እነዚህ በሸዋ የነበሩት የይኩኖ አምላክ ተከታይ ነገሥታት በሸዋና በሸዋ ዙሪያ አገር ሲያቀኑ ክርስትናን ሲያስፋፉ ክርስትናው እንዲጠበቅ ባቀኑት አገር ቤተ ክርስቲያን ይተክላሉ ። በተለይ ደግሞ የአባቶቻቸው መደበኛ አገር በሆነው በዚህ አሁን ንጉሡ ከሸዋ ሸሽተው በመጡበትና አሁን በተሸሸጉበት በቤተ አምሐራ አገር በልዩ ልዩ ቅዱሳን ስም ብዙ አብያተ ክርስቲያን አሠሩ ። ይህ የአምሐራ አገር ብዙ ጊዜ መጽሐፉ ቤተ አምሐራ የሚለው ወዴት እንደሚገኝ በካርታው ሥዕል ላይ መመልከት ይበቃል ። ይኸም አገር ከጋላ ሥሪት

(1) የባሴት ሬኔ ማስታወሻ ቁጥር 119 (የኢት. ታሪክ ጥናት ገጽ 141)

ወዲህ እየጠበበ አማራ ሳይንት የተባለው ብቻ እስከዛሬ ሲቀጥል የቀረው የወሎ ግዛት የሚባለው ነው ። ይህ ያማራ አውራጃ በዚያን ጊዜ ስፋቱ ከቤገምድር ግዛት አንሥቶ እስከ ግድም ድረስ ሰፊና ታላቅ አውራጃ መሆኑን የባዕዱ ጸሐፊ ዓረብ ፋቂህ ሳይቀር የጻፈው ትዝ ይለናል ።

በዚህ ሰፊ ግዛት ላይ መካነ ማርያም ፤ ግሼን ማርያም ፤ ደብረ እግዚአብሔር ፤ ደብረ እስጢፋኖስ (ሐይቅ) ፤ ገነተ ጊዮርጊስ ፤ መካነ ሥላሴ ፤ አትሮንስ ማርያም ፤ ደብረ ነጐድጓድ መካነ ሰማያትና ሌሎችም አሉ ።

ከነዚህ ውስጥ በታሪክ ውስጥ በጽሑፍ ተገኝቶ አሠሪዎቹ የታወቁት ለምሳሌ ያህል ቀጥለው ያሉት ናቸው ።

፩ኛ. የሐይቁ ደብረ እስጢፋኖስ ተካዩ የመጨረሻው የአክሱም ንጉሥ ድልነዓድ ነው ፤ የተተከለበት ጊዜ ፯ሺ፫፻፶፪ ዓመተ ዓለም ሲሆን ከዓመተ ዓለሙ ዓመተ ምሕረቱ ሲለይ ፫፻፶፪ ዓ. ም. ይሆናል ። በዚህም ዘመን የነበሩት ግብ ጻዊው ጳጳስ ዳግማዊ አባ ሰላማ ናቸው ።

ይኸን ታሪካዊ ጽሑፍ የሚሰጠን የአባ ኢየሱስ ሞዓ ገድል ነው ። ይኸም ገድል ሁኔታውን ከሥር ሲያመጣው በተለመደ ገድላዊ አነጋገር እንደዚህ ይላል «. . . . . የእስጢፋኖስ ሕንፃ ከመመሥረቱ በፊት በደሴቱ ውስጥ ባሉጥ የሚባል ትልቅ ዛፍ ነበር ። ከርሱም ግርጌ ሕዝቡ የላም ሥጋና ወተት እየ ገበረ የሚሰግድለት ዘንዶ ነበር . . . . . ፳፩ዝመሪያው ጳጳስ ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ወዲህ ሁለተኛው አባ ሰላማ መጥቶ ሕዝቡ ለዘንዶው እንደሚ ሰግድ ስለነገሩት መስቀሉን አውጥቶ ሠፈሩን በባረከው ጊዜ ዘንዶው ጠፋ ። ከዚህ በኋላ ተመልሶ የደሴቱን መልካምነት ላዔ ድልነዓድ . . . . . ነገረውና ንጉሡ መጥቶ ከደሴቱ በቀኝ በኩል የደብረ እግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ሠራ ። . . . . ቀጥሎ በደሴቱ ውስጥ በ፯ሺ፫፻፶፪ ዓመተ ዓለም (፫፻፶፪ ዓ. ም.) አንዲት ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሕንፃ መሥራት ዠመረ . . . . . . ። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥራው ተፈጽሞ በማን ታቦት ይሠየም በመላእክት ወይም በጻድቃን ወይስ በማርያም እያሉ ሲጠያየቁ . . . . . . ከኢየሩሳሌም በድብቅ የመጣ በላዩ ይህ ታቦት የመዠመሪያው ሰማዕት የእስጢፋኖስ ነው የሚል ጽሑፍ ያለበት ስለተገኘ . . . . . . ንጉሡ ለደብረ እግዚአብሔር እንዳ ደረገው ታላቅ በዓል አድርጎ ታቦቱ ገብቶ ደሴቱን ደብረ ነጐድጓድ ብሎ ሠየመው ። ለገዳሙም ፫፻ ትክለኛ ካህናት መድቦ ለቤተ ክርስቲያኑ መተዳ ደሪያ ብዙ አገር የከበረ ልብስም . . . . . . ሰጠ»

ያባ ኢየሱስ ሞዓ ገድል ስለ እስጢፋኖስ ገዳም አተካከል ይኸን ከዚህ በላይ ያለውን ካመለከተ በኋላ የዚሁ ገዳም አበ ምኔት (መምህር) ስለነበሩት ስለአባ ኢየሱስ ሞዓ ሲጽፍ በዚች አገር ዘክርስቶስ የሚባል ከሚስቱ ከእግ ዚእ ክብራ ጋር በመሃይምንነት ሲኖሩ . . . . ኢየሱስ ሞዓ ፤ ገብረ ጽዮን ፤ ስቡሕ አምላክ የሚባሉ ሦስት ልጆች እንደወለዱ . . . . . ከነዚህ መካከል ኢየሱስ ሞዓ በግንቦት ፳፮ ቀን ረቡዕ ፲፪፻፮ ዓ. ም. ከተወለዱ በኋላ ፴

ዓመት በእናት በአባታቸው ቤት እየተማሩ እንዳደጉ ቀጥሎ ወደ ደብረ ዳሞ ይምጸእ ምሕረት ከሚባለው ጋር ሄደው ከገዳሙ መምህር ከአባ ዮሐኒ ዘንድ ምንኵስናን ተቀብለው ፯ ዓመት እንደኖሩ ከዚያ ወደ ደብረ ሐይቅ ተመልሰው ያገሩ ተወላጅ ኄር እምላክ ወደ ደሴቱ ውስጥ መርቶ እንዳስገባ ቸው በዚያም ሲኖሩ ነዋሪዎቹ ትጋታቸውን ፣ ምግባራቸውንና ትሕትናቸ ውን ስለተመለከቱ በዘመኑ ወደነበረው ወደ ዛጐዬ ንጉሥ ልከው መምህራ ቸው ይሆኑ ዘንድ እንዳስፈቀዱላቸው ገድላቸው ያመለክታል (1) ።

በኢትዮጵያ ስመ ጥሩ ገዳም ሲተከል በዚያው ላይ ገዳሙን በመምህር ነት የሚመሩት በሚሠሩት የሃይማኖት ምግባር ምክንያት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በያውራጃው ይነሣሉ ።

ደብረ ዳሞን አክሱማዊው ንጉሥ ዓፄ ገብረ መስቀል ከገደሙት ወዲህ በዚህ ገዳም አቡነ አረጋዊ ስመ ጥር ሆነው እንደኖሩና የደብረ ዳሞ ገዳም በስማቸው ደብረ አባ አረጋዊ እንደተባለ በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስ ሞዓ በሐይቅ ተወልደው ባደጉበት ሰዓት የዚህ የደብረ ዳሞ ገዳም አበ ምኔት አባ ዮሐኒ በጣም ስመ ጥር ናቸው ። አባ ኢየሱስ ሞዓን አስተምረው እስኬማ አልብ ሰው ሰቅ አስታጥቀው ሲያመነኵሱ ለአባ ኢየሱስ ሞዓ እንደ አባት ናቸው ። እንደዚሁም አባ ኢየሱስ ሞዓ የሐይቁ መምህር በነበሩበት ሰዓት በሸዋ የቡ ልጋው ተወላጅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ኢየሱስ ሞዓ ምንኩስናን ተቀ ብለው ከአባ ዮሐኒም ከተገናኙና በሐይቅ ያደገውን ይኩኖ አምላክን ለንጉ ሥነት ስላበቁ እርሳቸው ደግሞ በበዓታቸው በደብረ ሊባኖስ ስመ ጥር ሆነዋል ።

ስለዚህ ፦

በደብረ ዳሞ አቡነ ዮሐኒ

በደብረ ሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ

በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

በደብረ ቢዘን አቡነ ፊልጶስ

ሌሎችም በያለበት ያሉት ገዳማትና አበ ምኔት ብዙዎች ስለሆኑ በዚህ ምዕራፍ ተዘርዝረው አያልቁም ።

ይህ ዛሬ በተሁለደሬ (ወሎ) የሚገኘው የደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም እላይ በተመለከተው ዓይነት ከተተከለ ወዲህ በአባ ኢየሱስ ሞዓ እጅ እየተማረ ያደገው ዓፄ ይኩኖ አምላክ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ በአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ደጋፊነት በዛጕዬዎች የተያዘውን መንግሥቱን ካገኘ በኋላ እርሱና ተከታዮቹ የተ ክለ ሃይማኖትን ገዳም ደብረ ሊባኖስንና የአባ ኢየሱስ ሞዓን ገዳም ደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስን አክብረው ለተክለ ሃይማኖትና ለተከታዮቻቸው የእጨጌነት ማዕርግ ከሲሶ መንግሥት ጋር ለአባ ኢየሱስ ሞዓና ለተከታዮቻቸው የዓቃቤ ሰዓትነት

(1) ገድለ ኢየሱስ ሞዓ ስታኒስላስ ኩር ያሳተመውን በየሥፍራው ተመልከት ።

ደረጃ እንደሰጧቸው የየአንዳንዳቸው ገድልና ታሪክ ነገሥት ያረጋግጣል ።

እንደ ደብረ ዳሞ ፣ እንደ አምባ ግሼን ያሉት ተራራና አምባዎች የግዞ ተኛ ማስቀመጫ እንደነበሩ የሐይቅ ደሴትም ከገዳምነቱ በቀር ዙሪያው በሙሉ በባሕር የታጠረ ስለሆነና ግዞተኛ ከዚያ ለማምለጥ ስለማይችል ምር ኮኛና ጥፋተኛ ይጋዝበት ነበር ። በዚህ ምክንያት ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ክርስቲያኖቹ ከሃይማኖታቸው ርቀው ደስክ ለሚባለው ጣዖት ሰገዱ ተብ ለው ከቤተ ሰቦቻቸው ውስጥ ሳይቀር ተክሠው በሞት የተቀጡ ጊዜ የንጉሡ ወዳጅ የነበረው ዓቃቤ ሰዓት ዘርዓ ጽዮን በሐሰት መስክሮ ብዙ ሰው ስላስገደለ በዚሁ የተንኮል ሥራው ዘርዓ ሰይጣን ተብሎ ወደዚሁ ሐይቅ በግዞት ተልኳል (1) ።

እንደዚሁም በዚህ የግራኝ ወረራ ሰዓት በአለፈው ዓፄ ልብነ ድንግል ከኤሚር ማኀፉዝ ጋር በ፲፰፻፸፰ ዓ. ምሕረት ተዋግተው ያሸነፉ ጊዜ አውራይ ሐርብ አራድ የሚባል የሡልጣን መሐመድ ዘመድ ተማርኮ በዚሁ በሐይቅ ደሴት ተገኝቶ አሁን በግራኝ አህመድ ወረራ ነፃ መውጣቱን እንመለከታ ለን ። ረኔ ባሴት አውራይ ሐርብ አራድ የተማረከው ሡልጣን መሐመድ ካዔ ናዖድ ጋር በተዋጋበት ጊዜ መሆኑን በማስታወሻ የጠቀሱት ስሕተት ይመስ ላል ። ምክንያቱም አሁን ግራኝ ሐይቁን በሚያስበዘብዝበት ዓመት (፲፭፻ ፳፬ ዓ. ም.) አውራይ ከደሴቱ ከገባ ፲፮ ዓመቱ ነው ስላለ ከ፲፮ ዓመት በፊት ያለው ዘመን ፲፰፻፸፰ ዓ. ም. ስለሆነ ይኸውም ልብነ ድንግል ከማኀፉዝና ከሡ ልጣን መሐመድ የተዋጉበት ዓመት ነው ። ደግሞም ናዖድ በዚህ ጊዜ ከሞቱ ፳፬ ዓመት ሆኗቸዋል (2) ።

የሆነ ሆኖ የነዚህን ገዳማት ያተካከላቸውን ሁኔታ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በላይ ያለውን ካመለከትን በኋላ የሁሉን መዘርዘር ስለማይቻል የቀሩትን እን ደዚሁ ዝርዝራቸውንና የተካያቸውን ስም ብቻ እያመለከትን አልፈን ወደ ቃጠሎውና ወደ ብዝበዛው እንተሳለፋለን ።

፪ኛ. ደብረ እግዚአብሔር ተካዩ ዓፄ ንዋየ ክርስቶስ (ስመ መንግሥቱ ሠይፈ አር እድ) ነው ፤ ዓረብ ፋቂህ ስናቃጥላት በላይዋ ላይ የተሠራችበትን ጊዜ የሚናገ ረው በሂጅራ ፯፻፸ ዓመት ያለውን ሙሴ ረኔ ባሴት እንደ ኤው. ቀ. ፲፫፻፴፪ አድርገውታል ። በኢትዮጵያ አቈጣጠር ፲፫፻፴፬ ወይም ፲፫፻፴፭ ዓ. ም. ይሆ

ISIC

(1) ለዘርዓ ጽዮንስ ዘተሠምየ ዘርዓ ሰይጣን በነቢበ ሐሰት ዘአቅተለ ብዙኃነ መነኮሳተ ወደባትረ ጠነሰሎ እደ ወአንስተ ሶበ ከሠተ ሎቱ እግዚአብሔር ብዙኃ ዓመፃሁ አመንኵሰዎ ወአግዓዝዎ ውስተ ሐይቅ ። የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ .... ዜና መዋዕል ። ገጽ 7 ፤ (በድጋሚ)

(2) ዓረብ ፋቂህ ..... ገጽ 168 ማስታወሻ ቍጥር 1 ፤

ናል ። ንዋየ ክርስቶስ የነገሠው በ፲፫፻፴፮ - ፲፫፻፸፭ ዓ. ም. መካከል የገዛበት ዘመን ፴፱ ዓመት ነው (1) ። በአለፈው እንዳነበብነው የአባ ኢየሱስ ሞዓ ገድል የደብረ እግዚአብሔርን የመገምመሪያውን ተካይ ድል ነዓድ መሆኑን ስለሚያረጋግጥ ምናልባት የፊተኛው ቤተ ክርስቲያን አርጅቶ ዓፄ ሠይፈ አርእድ ያሁኑ ሕንፃ አሠሪ ይሆናል ።

፪ኛ. ደብረ ነጐድጓድ ተካይ ዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ የነገሡበት ዘመን ፲፬፻፴፬ - ፲፬፻፷፰ ዓ. ም. የገዙበት ዘመን ፴፬ ዓመት ፤

፫ኛ. አትሮንስ ማርያም ተካዩ ዓፄ በእደ ማርያም ናቸው ። ከዚህ በፊት ንዋየ ክርስቶስ (ሠይፈ አርዕድ) ለማሠራት አስቦ መሬቱን ገዝቶ በመካከሉ ሞተ፣ ቀጥሎ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደብረ ብርሃን (ተጉለት) ሳሉ ስሟን ጴራቅሊጦስ ብለው ታቦት ልከው ታቦቱ ባንድ ቤት እንደተቀመጠ ሳያሠሩ ሞት ስለቀደማቸው ልጃቸው በእደ ማርያም አሠሩት ። በእደ ማርያም የነገሡበት ዘመን ፲፬፻፷፰ - ፲፬፻፸፰ ዓ. ም. የገዙበት ጊዜ ፲ ዓመት ነው (2) ። ዓረብ ፋቂህ ዘርዓ ያዕቆብ አሠሩት ያለው ስሕተት ነው ። አትሮንስ ማርያም የተተከለችበት ሥፍራ የቀድሞ ስሙ ከላንቶ ነበር ። በእደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ሲጨርሱ ከእንግዲህ ወዲያ ይህች ቦታ ከላንቶ መባሏ ቀርቶ አትሮንስ ማርያም ትባል አሉ ። (ገጽ 119)

፬ኛ. ገነተ ጊዮርጊስን ዓፄ እስክንድር ነው ያሠራው ። ይኸን የሚያረጋግጠው በዘመኑ ወሬ እየጠየቀ የጻፈው የዓረቡ ጸሐፊ ነው (3) ። የዚህ ንጉሥ ዜና መዋዕል ግን "ንጉሣችን (እስክንድር) እንደገና ከሸዋ ሄዶ በአምሐራ አገር ደርሶ ሥራውን ሁሉ እየዞረ ተመለከተ ። ገነተ ጊዮርጊስን ደብረ ነጐድጓድን አትሮንስ ማርያምን ጐበኛቸው" እያለ መጐብኘቱን እንጂ ገነተ ጊዮርጊስን ማሠራቱን አይገልጽም በሌላ ቦታ ላይ (በግድም ወይም በይፋት ?) ግን ደብረ ምሥዋዕ ብሎ የሠየማትን ቤተ ክርስቲያን በእጁ መሥራቱንና ቤተ ክርስቲያኒቱንና ካህናቱን እንዳከበራቸው ይገልጻል (4) ። ዜና መዋዕሉ ቁንጽል ታሪክ የያዘ በመሆኑ ከርሱ ይልቅ በዚያው በቃጠሎው ሰዓት የየአንዳንዱን ሠሪ ንጉሥ እየጠየቀ የጻፈውን የዓረቡን ጸሐፊ ማመን ስለሚቻል ገነተ ጊዮርጊስንም ያሠራው ዓፄ እስክንድር ነው ማለት ነው ።

፭ኛ. መካነ ሥላሴን ዓፄ ናዖድ አስገምረውት ስለሞቱ ልጃቸው ዓፄ ልብነ ድን

(1) የረኔ ባሴት ማስታወሻ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ገጽ 326 - 329 ቍጥር ፤
(2) የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብና የዓፄ በእደ ማርያም ዜና መዋዕል በኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 44 ገጽ 230 - 234
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 314
(4) ወሃሊፎ ኀዐበ ንጉሥን (እስክንድር) እመንገለ ሸዋ በጽሐ ምድረ አምሐራ ። ወዖዶን ኵሎን መካናት ወሐወጾን ለገነተ ጊዮርጊስ ወደብረ ነጐድጓድ ወለአትሮንስ እግዚእትነ ማርያም . . . . . የእስክንድር ዜና መዋዕል Jules Perruchon ያሳተመው ገጽ 340 - 343
(ወመቅደሰሰ ሐነጸ በእደሁ እምድኅሬሁ እንዘ ይሰሚ ስማ ደብረ ምሥዋዕ ወረሰያ ክብርተ . . . .)

ግል በሚገባ አሠርተው አስጊጠው አስጨረሱት ። በ፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ሥራው አልቆ ዓፄ ልብነ ድንግል ታቦቱንና ያባታቸውን ዐጽም በጥር ወር ካሮጌው ቤተ ክርስቲያን ወዳዲሱ ሕንፃ አዛውረው ሲያስገቡ በታላቅ በዓል ቅዳሴ ቤቱን ባስከበሩበት ሰዓት እንግዶቹ ፖርቱጋሎች እነአልቫሬጽ እንደነበሩ ዕድሜያቸው መቶ ዓመት ያለፈው ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ በሁለት ሰዎች ተደግፈው ቆመው እንደተካፈሉ ያዬ በእደ ማርያም ባለቤት ንግሥት እሌኒ ፣ የንጉሡ እናት ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ፣ ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል እን ደነበሩ በበዓሉ ላይ የነበረው አልቫሬጽ በመጽሐፉ ያረጋግጣል (1) ።

ነገሥታቱ ሁል ጊዜ በዘመናቸው ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ በጊዜያቸው የሚ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን አባታቸው ወይም ከነርሱ በፊት የነበረው ማናቸውም ንጉሥ ካሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዲበልጥ ይጥራሉ ፣ ለዚሁ ጉዳይ ለሥራውም ሆነ ለንዋየ ቅዱሳቱ ብዙ ሀብት የሚወጣበት ምክንያት ስለዚህ ነው ።

ይኸው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በ፲፭፻፲፫ ዓ. ም. ላይ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድን ግል አሠርተው የጨረሱትን ቤተ ክርስቲያን ለመመረቅ ንጉሠ ነገሥቱን አጅበን በሄድን ጊዜ በዚያው አቅራቢያ የሚገኘውን የንጉሡ እናት (ናዖድ ሞገሳ) ያሠሩ ትን ቤተ ክርስቲያን እንድንጎበኝ ንጉሡ አዘውን ወደዚያው ሄድን ይልና ከዚሁ አያይዞ በምንጎበኝበት ሰዓት በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ምንም ዓይነት እንከን እንዳና ወጣ ሹማምንቱ አስቀድመው አስጠነቀቁን ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያኑ ላይ እንዳች ጉድለት አለበት በማለት ለእቴጌዪቱ ቢነግሯቸው ወይም ከልጃቸው ቤተ ክርስቲያን አይተካከልም ቢሏቸው እንግዲያውስ ይኸ ፈርሶ ሌላ ይሠራ ለማለት ስለማይመለሱ ነው ይላል (2) ። ስለዚህ እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ይህ ቤተ ክርስቲ ያን ቤተ ሰማያት ነው ያሠሩትም የንጉሡ እናት ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ናቸው የተቀ በሩበትም እዚያው ነው (3) ።

እላይ እንደተመለከትነው አንዱ ንጉሥ ከሌላው እያስበለጠ በየጊዜው ያሠ ራው ከዚህ ዘመን ደርሶ በተለይ ዓፄ ናዖድ አዠምረውት ዓፄ ልብነ ድንግል አሠር ተው ያስጨረሱት የመካነ ሥላሴ ሥራ ይበልጣል ። ስለሥራው አኳኋን በዓቃቢ ሰዓቱ መሪነት የጐበኘው አልቫሬጽ እንደዚህ ይላል «ግድግዳዎቹ በጥርብ ደንጊያ ተሠርተው በሐረግ አጊጠዋል ። በውስጥ ላያቸው ሰው ለመዠመሪያ ጊዜ ማለፊያ መስለው ቢታዩም . . . . . . የማዕዘን ድንጋዩና ትንንሾቹ ድንጊያዎች በደረቅ ካብ ስለተሠሩ የጣርያው ማዋቀሪያ እንጨት በግድግዳው አያልፍም ።

እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (ገነተ ጊዮርጊስ) የዚህም ዋናው የበር መዝጊያ በወርቅና በብር ተለብጦ.ል በወርቁ ልብድ ውስጥ አንዳንድ የከበሩ ደንጊ ያዎች . . . . . . አሉ ። ጣራዎቹ በስድስት ምሰሶዎች ላይ አርፈዋል ። . . . . . .

(1) Verdadeira: በነአቶ ግርማ ትርጉም ምዕ. 100
(2) ” ” ” ” ” ” ” ምዕ. 95
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 313

በውጭ ታዛውን ፳፭ ረገኸርም ምሰሶዎች ይግፈውታል . . . . . . በሰገነቱ ዙሪያ እያንዳንዳቸው ከ፲፮ ቅጽ በወርቀ ዘቦ ጨርቅ የተሠሩ ፲፮ ተከፋች መጋረጃዎች አሉ . . . . . . .» (1) ።

ያገሩንና የአውሮፓን አብያተ ክርስቲያናት (ካቴድራል) ሕንፃ የሚያውቀው ካህኑ አልቫሬጽ ስለዚህም ስለሌሎቹም አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃና ውስጣ ውስጥ ሥራ ከፍ ያለ አድናቆት አላደረበትም ፤ በዚህ ምክንያት ጐብኝተን ስንመለስ ስለሥራው አስተያየታችንን ንጉሡ ቢጠይቀን "የማን መሆኑን ስለምናውቅ ውብ ነው" ብለን መለስንለት ይላል ። ይኸንንም ማለቱ በይሉኝታ ብቻ አደነቅን ማለቱ ነው ።

ነገር ግን ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በጣም የተደነቁ ግራኝ አህመድና ሹማምንቱ ናቸው ። በነርሱ ዘንድ በሐረርና በአዳል ፤ በሱማሌ ፤ በዓረብ አገርም ቢሆን ይኸን የመሰለ ሥራ ስለሌለ በእርግጥ ሊያስደንቃቸው ይችላል ። በዚህም ላይ እነ አልቫሬጽ የጐበኙት በ፲፭፻፲፫ - ፲፬ ዓ. ም. ሲሆን ግራኝ የደረሰው ግን በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. ስለሆነ በመካከሉ የአሥራ አንድ ዓመት ጊዜ ስላለ በዚህ ጊዜ ውስጥ ግራኝን ሊያስደንቀው የቻለ አንዳንድ በየጊዜው የተጨማመረበት የጌጣጌጥ ሥራ ይኖር ይሆናል ።

ስለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በዚሁ ጊዜ ከግራኝ ጋር የነበረው ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ ከዚህ[illegible]ቅሎ ያለውን ዝርዝር ይሰጣል ። «በዚህ በቤተ አምሐራ በሀበሻ ምሳሌ የሌላት (ማንም የማይተካከላት) አንዲት ቤተ ክርስቲያን አለች ። እርሷን ያሠራት የወናግ ሰገድ አባት ንጉሡ ናዖድ ነው ። የርሷ ሥራና ጉጥ ፲፫ ዓመት ፈጀበትና ሳይጨርስ ስለሞተ ልጁ ወናግ ሰገድ ከአባቱ አስበልጦ ፳፰ ዓመት ሙሉ አሠርቶ አስጨረሳት ። ሁለመናዋ በወርቅ የተለበደ ስለሆነ እንደ እሳት ታንጸባርቃለች ። በውስጧ ያለው ጸሐል ሰንና ብርት የወርቅና የብር ነው ። ስፋቷ መቶ ክንድ ቁመቷ ግን ከመቶ ሃምሳ ክንድ ይበልጣል ። ሁለመናዋ በጉጠኛ እንጨትና ደንጊያ በወርቅና በከበረ ደንጊያ የተለበደ ነው ። ስሟ በክርስቲያኖች ቋንቋ መካነ ሥላሴ ትባላለች ትርጓሜውም የሦስቱ አማልክት መቀመጫ ማለት ነው ። ነገር ግን አምላክ ከዚህ ሥፍራ ዐይላይ ነው ያለው (በሰማይ) ራሱ አንድ ብቻ (ዋሕድ) የማይወለድ ያልተወለደ እኩያም የሌለው ነው ። በዚች ቤተ ክርስቲያን የዘርዓ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የእድማስ (በእደ ማርያም) ልጅ የናዖድ መቃብር አለ . . . » (2) ።

ዓረብ ፋቂህ እዚህ ላይ ነገሥታቱ የነገሡበትን ጊዜ በሙሉ ለዚሁ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የመደበው ይመስላል ። ዓፄ ናዖድ ፲፫ ዓመት ፈጀበት ሲል የነገሡበትም ሙሉው ጊዜ ይኸው ነው ። ዓፄ ልብነ ድንግል ፳፰ ዓመት ሙሉ አሠራት ሲል ከነገሡ ዠምሮ እስከዚህ እስላሞቹ እስኪ ደረሱበት ጊዜ ድረስ ፳፫ ወይም ፳፬ ዓመት ስለሆነ አባትና ልጁ የነገሡበትን ፴፮ ዓመት ጊዜ ለዚሁ ሥራ እንዳዋሉት አስመስሎታል ።

(1) አልቫሬጽ በነአቶ ግርማ በሻህ ትርጉም ምዕ 95 ገጽ 234
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 281 - 282

መካነ ሥላሴ ተብላ መሠየሚን ትርጉሙን ራሱ የሦስቱ አማልክት መቀመጫ ብሎ ተርጉሞ አምላክ የማይወለድ ያልተወለደ እኩያም የሌለው አንድ ብቻ ነው በማለት የኛዎቹን እግረ መንገዱን ለመንቀፍ በዚህ ሥያሜ ተጠቅሞበታል ። እዚህ ላይ ባይረዳው ይሆናል እንጂ የኛዎቹ ሠለስቱ አካላት አሐዱ መለኮት ይላሉ እንጂ ሦስት አማልክት በፍጹም እንደማይሉ በሃይማኖተ አበውም በምሥጢረ ሥላሴም አረጋግጠዋል ። እግዚአብሔር እኩያ እንደሌለው በኢዮብ ምዕ. ፴፮ በሕዝቅኤል ምዕ. ፵ በ፩ኛ ነገሥት ምዕ. ፫ የተጻፈውን ሁለቱም ወገኖች (ክርስቲያኖቹም እስላሞቹም) ያምናሉ ። ነገር ግን በጌታ (በአምላክ) ልደት ተካክደዋል ። የዚህ ሁሉ ጦርነትና ሁካታ ቃጠሎና ረብሻ ምንጭ ከሆነው አንዱም ይኸው የእምነት ልዩነት የፈጠረው ጥላቻና ጠብ ነው ።

የሆነ ሆኖ ነገሥታቱ እቴጌዎቹ በነርሱም ዙሪያ ያሉት መሣፍንትና መኳንንት ሳይቀሩ እንደዚህ አድርገው ላሠሩት ቤተ ክርስቲያን ከሕዝብና ከነገድ ከባላባት ከአገረ ገዥ ከነጋዴም ይሁን ከገበሬ በቀረጥም በመታያም በውርስም የገባላቸውን ወርቅና ልብስ በየጊዜው እየሠጡ ያበለጥጉታል ። ከዚህ የወርቅ ሀብት ወደ ሕንድ ወደ ፋርስ ወደ ዓረብ አገር እየላኩ ልዩ ልዩ አልባሳትና ንዋየ ቅድሳት ሥጋጃም በግዢ እያስመጡ ያከብሩታል ። ለሌላው ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ፣ ለመኳንንት ስጦታ የማይሰጡትን ለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚውል ሲሆን ግን እንጸድቅበታለን ብለው የሚያምኑበት በምድር በሕይወትም ከሕይወት ወዲያም ስማቸው የሚጠራበት በመሆኑ አይሰስቱም ። ISIC

ራሳቸው መስጠት ብቻ ሳይሆን እነርሱ ለተከሉትና ለደበሩት ቤተ ክርስቲያን ለገደሙት ገዳም ሌሎቹ መሣፍንትና መኳንንት ከሀብታቸው እየከፈሉ ሲሰጡ ላቸው ሰጭዎቹ በነገሥታቱ ዘንድ ሞገስና ባለሟልነትን ከዚያም በየምክንያቱ ሹመትን ሽልማትን ያገኙበታል ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ንጉሠ ዓፄ ልብነ ድንግል ለመካነ ሥላሴ ፬፻፶ የካህን ትክለኛ አድርገው ከሌላው ሁሉ አብልጠውታል ።

ምዕራፍ ፳፪

የአብያተ ክርስቲያናቱ አለቆች ወግና ማዕረጋቸው ።

የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት የሹመትና የማዕርግ የወጋ ወግ ብዛት እንደ አገራችን እንደ ኢትዮጵያ የበዛበት አገር ቢኖር በምሥራቅ አገሮች በቻይናና በሕንድ በጃፓንና በፋርስ ይሆናል ። በተለይ በዚህ በ፲፱ኛው መቶ ዓመት ከንጉሡ ዠምሮ እስከ ባሻ ፣ ከጳጳስ ዠምሮ እስከ ዲያቆን ያለው የማዕርጉ ስም በራሱ ላይ የሚደፋው ራስ ወርቅና አክፋር ፣ በውስጥና በላይ የሚደራርበው ቀሚስና ካባ ድርብ ኩታ የሚታጠቀው የሱሪው የድጉ የጕራዴው ዓይነት የሚጫመው ጫማ የሚቀመጥበት የበቅሎ ዕቃ ዓይነት በራሱ ላይ የሚያዝለት ጥላ ወይም ድባብ የሚበላበት

ገበታ ፣ ሥጋ የሚቆርጥበት ቢላዋ ፤ ጠጅ የሚጠጣበት ብርሌ እንደ ማዕርጉና እንደ ተዋረዱ ብዙ ነው ። ይኸንንም እዚህ ላይ መዘርዘር ጊዜ ስለሚፈጅ የቅርቡን ጊዜ ክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ በዝክረ ነገር መጽሐፋቸው ያሠፈሩትን ማን በብ ይበቃል (1) ።

ይኸም ሁሉ በየዘመኑ የማዕርጉ ስም የሽልማቱም ዓይነት ብዙ ጊዜ ቢለዋ ወጥም ዞሮ ዞሮ መደቡንና አሳቡን አይለቅም ። በቤተ ክህነት ረገድ ያለውም የማዕ ርግ ስም እንደዚያው እንደ ቤተ መንግሥቱ ዓይነቱ የበዛ ነው ። የቤተ ክህነቱ ባለ ሥልጣኖች ሥልጣናቸው የሚደክምበትና የሚገንበት ዘመን አለ ። ብዙ ጊዜም ንጉሡ መንፈሳዊነት ሲሰማው የቤተ ክህነትን ሰዎች ፣ ወታደራዊነት ሲሰማው የጦር ባለሥልጣኖችን ከፍ የሚያደርግበት ጊዜ አለ ።

የሆነ ሆኖ በጠቅላላው በተለይ በዚህ በ፲፬. ፲፭. ፲፮ኛው መቶ ዓመታት ውስጥ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ከቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ቅድሚያ ያላቸው ይመስላል ። ስለሚያነቡ ፤ ስለሚተረጉሙ ፣ የመንፈሳዊውንና የነፍሱን መንገድ ስለያዙ ክብራቸውን ለማዋረድ የሚነሣ እምብዛም የለም ፣ እነርሱንም ያዋረደ አምላክን እንዳዋረደ ይቆጠራል ። በተለይ ደግሞ ዓፄ ልብነ ድንግል ከወ ታደርነት ይልቅ መንፈሳዊነት ስለሚሰማቸው ከመንግሥቱ ሥራ የተረፈውን ጊዜ ያቸውን የመንፈሳዊ መጻሕፍት በመመልከት የዚህኑ ጉዳይ ከቅርብ አማካሪያቸ ውና ከመምህራቸው ከዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ጋር አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥ እንደሚያሳልፉ ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

ISIC

በዚህ በቤተ አምሐራ (የዛሬው ወረይሉ) ዓፄ ልብነ ድንግል ያሠሩት የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ስሙን ሳይጠቅስ «ዓቃቤ ሰዓቱ ነው ፣ እኛንም ያስጐ በኘን እርሱ ነው» ብሎ አልቫሬጽ ስለሚያረጋግጥ በእርግጥ ያው ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ነው (2) ። የዚህ የዓቃቤ ሰዓት ማዕርግ ከን ጉሡ ቀጥሎ ከቢትወደዶች ፤ ከራሶች በላይ መሆኑ ሲታወቅ የሚለብሰውን የማዕር ጉን ልብስ በዚያን ሰዓት ባለው አጠራር ዝርዝር ማቅረብ አንችልም ። ነገር ግን ከንጉሡ ጋር ከመመሳሰሉ የተነሣ እስላሞች ወደፊት በዓባይ ወንዝ ዳር ንጉሡን ያገኙ መስሏቸው ይዘው መግደላቸውን እናነባለን ።

ከ፲፬፻፺ እስከ ፲፭፻፳ ዓ. ም. የነገሠው ዓፄ በእደ ማርያም የአትሮንሰ ማርያ ምን የቤተ ክርስቲያን ሥራ በሚያምር አኳኋን አሠርቶ ጨርሶ የእመቤታችንን ታቦት አስገብቶ ቅዳሴ ቤቱን ከአከበረ በኋላ ለዚች ቤተ ክርስቲያን የበላይ አለቃ ዓምዱ የሚባለውን መርጦ ወጉንና ሥርዓቱን ለይቶ እንደሾመው የራሱ ዜና መዋ ዕል ይገልጻል ። በርሱም የሌሎቹን የመሰሎቹን መረዳት ይቻላል ማለት ነው ።

(1) ዝክረ ነገር ምዕ. ፲ ገጽ 660 - 680
(2) አልቫሬጽ ገጽ 269

ከዚሁ ዜና መዋዕል ላይ ተውጣጥቶ በአማርኛ ተተርጉሞ የአትሮንስ ማርያም አለቃ ወጉና ሥርዓቱ ልብሱ ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል ።

ሀ - የአለቃው የማዕርግ ስም መክብብ

ለ - ልብሱ በብርና በወርቅ የተጌጠ ባለወርቅ ቁልፍ የሆነ ካባና ቀሚስ ፤

ሐ - በራሱ የሚደፋው እንደ ጐፈር ያለ (ክልኤቱ አክፋር) ያሉበት በጽጌ ረዳ ቀለም ያጌጠ የወርቅ አክሊል ፤

መ - ከራሱ በላይ የሚያዝለት የአማረ ድባብ

ሠ - ከፊቱ የሚቆሙለት ፲፪ መስቀል የያዙ (ቀሳውስትና ዲያቆናት)

ረ - የሚጋርዱለት የጤጤ ሰዎች (ሰብአ ጤጤ) (1) ።

ሰ - የሚጠጣበት ባለ ቀለም ብርሌ ፤

ቀ - ሥጋ እየቆረጠ የሚበላበት የብር ቢላዋ ።

የአለቅየውን እንደዚህ አድርጎ ወግ ማዕርጉን የሚበላበትንና የሚጠጣበትን መሣሪያ ጨምሮ ከወሰነ በኋላ ለካህናቱና ለቀሳውስቱ፡ መተዳደሪያ የእመቤታችን በዓል በዋለበት ቀን ለበዓሉና ለግብሩ መደገሻ የሚሆን ሰፋፊ ርስት መትከሉንና ከልጅነቱ ዠምሮ እስኪነግሥ ከነገሠም በኋላ ያጠራቀመውን ወርቅና ብር ሀብቱን በሙሉ ለዚች ቤተ ክርስቲያን ሰጥቶ በሀብት ፤ በክብር ፤ በሥርዓት ከሌሎቹ የበለጠችና የገነነች እንድትሆን መጣጣሩን ዜና መዋዕሉ ይገልጻል (2) ።

ISIC

በእደ ማርያም በዘመኑ ይኸን ሠርቶ ሲያልፍ በዚህ በግራኝ ወረራ ጊዜ ደግሞ የነበሩት የበእደ ማርያም የልጅ ልጅ ዓፄ ልብነ ድንግል የመካነ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ከአባቶቻቸው አስበልጠው አሠርተው ዕልቅናውንም ጳጳሱና እጨጌው ሳይቀጠሩ ማዕርጉ ከሁሉ በላይ ለሆነው ለዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ሰጥተውታል ። በውስጡ የሚያገለግሉት የቀሳውስትና የካህናት ቊጥር ትክሉ ፬፻፶ መሆኑን ይኸም ቊጥር ከሌላው ትክል ሁሉ መብለጡን ደራሲው ያልታወቀ የሚያረጋግጥ የአማርኛ ጽሑፍ አለ ።

እንግዲህ ግራኝ አህመድ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ከቤተ አምሐራ ተያይዞ በስተደቡብ ከዋያት ወንዝ ወዲህ በመንዝ በግድም በይፋት በተጉለት በፈጠጋር በደዋሮ በእንደገብጣን ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ስመ ጥሩውን ደብረ ሊባኖስን ምስሐለ ማርያምን ሁሉ አዘርፎ አቃጥሎ ከጨረሰና ንጉሡን በዋስል ድንገተኛ አደጋ ጥሎ በአባረረበት ዓመት በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. እነዚህን ስመ ጥር አብያተ ክርስቲያናት መዠመሪያ የደለበ ሀብታቸውን ከአስዘረፈ በኋላ እንደምን እያቃጠለ አመድ እንዳደረጋቸው በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመልከት ።

(1) የወዴት አገር ሰዎች መሆናቸው አይታወቅም Pereira ያሳተመው ያዔ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ብዕለ ክርስቶስኒ ነበረ በአምባ ዘትሰመይ ጤጤ ይላል በጐጃም ጐን ያደርገዋል ምዕራፍ ፰።

(2) የኢ.ት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 45

## ምዕራፍ ፳፫

### መካነ ሥላሴ ፣ አትሮንስ ማርያም ፣ ደብረ ነጐድጓድ ኅዳር ፯ ቀን ፣ ቤተ ሰማያት ፣ ገነተ ጊዮርጊስ ኅዳር ፲፪ ቀን ደብረ እግዚአብሔር ታኅሣሥ ፯ ቀን (፲፭፻፳፱ ዓ. ም.) እየተዘረፉ እንደተቃጠሉ ።

ባለፈው ምዕራፍ በዋስል ተራራ በተለይ ሐን በተባለው ሥፍራ ንጉሡ ሠፍረው ሳለ ግራኝ አህመድ እያደባ ድንገት ደርሶ አደጋ ጥሎ እንደምን እንደተዋጋቸው ንጉሡም በምን አኳኋን ሸሽተው እንዳመለጡ አንብበናል ። እንግዲህ እነዚያን ለመከላከያ ምሽግ የነበሩትን የአህያ ፈጅንና የምችግን ተራራዎች በመሪና በጠቋሚ አልፎ ንጉሡን ከአባረረ በኋላ ግራኝና ጦሩ በቤተ አምሐራ ገብቶ እነዚያን ባለፈው ምዕራፍ ያነበብናቸውን አብያተ ክርስቲያናት እየዘረፈ ለማቃጠል ምንም የሚያግደው ኃይል የለም ። የኢትዮጵያ ኃያላን በአይፈርስና በፈጠጋር ፣ በሸምብራ ኩሬ ፣ በገዘሆን ዱር ፣ በደዋሮ ወድቀዋል ። የተረፉት የራሳቸውንም የንጉሡንም ሕይወት ለመጠበቅ በንጉሡ ዙሪያ ሆነው ወደ ጐጃም አምርተዋል ፤ ግማሹ የግራኝ ምርኮኛ ሆኖ ታስሯል ፤ የፈራውም እየገባ ታማኝ ሆኖ ሰልሞ ለአዲሱ ገዥ ታዛዥና መሣሪያ ሆኗል ።

ስለዚህ የነዚህን የታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ሀብታቸውን ለመዝረፍና ለማቃጠል ግራኝና የጦር አለቆቹ እገሌ በዚያ እገሌ በዚህ እየተባባሉ ተከፋፍለው እንደምን እንዳቃጠሉት ሲያስረዳን ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ይላል ።

ISIC

«ጦርነቱ በተጀመረ በሦስተኛው ቀን ይማም (ከዋስል) ወደቤተ አምሐራ ሄዶ ላሊበላ ከሚባል ሥፍራ ላይ አደረ ። ከብርዱ የተነሣ ውሀው ሁሉ በረዶ ስለሆነ ብዙ እስላሞች እየጠጡ ሞቱ . . . . . ከላሊበላ ተነሥተው ሲሄዱ . . . . . (1) የንጉሡ ቤተ ክርስቲያን ታየች ። በዚያን ጊዜ መሪው ቆም አለና የንጉሡ ቤተ ክርስቲያን ይህች ናት እነሆ ደረስን ብሎ ለይማም ነገረው . . . . . . . ። እኋላ ያለው ጦር እስኪደርስ እየጠበቀ ይማም መሪውን በዚህ ቀበሌ ስንት አብያተ ክርስቲያናት አሉ ብሎ ቢጠይቀው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እየዘረዘረ ቆጠረለት ።

ከዚህ በኋላ ይማም ወደ አትሮንስ ማርያም ወዚር ኑር ኢብራሂምን ፣ ወደ ደብረ ነጐድጓድ ሲዲ መሐመድን ፤ ወደቤተ ሰማያት ባሻራህ ቤን ጐሹን ላከና እርሱ ራሱ ወደ መካነ ሥላሴ ሄዶ እቅጽሩ አጠገብ በደረሰ ጊዜ ቆም ብሎ ከጓደኞቹ ጋር እያየ አደነቀና ወደ ውስጡ ገባ ። በወርቅና በብር ያጌጠች ቤተ ክርስቲያን ናት ። የከበረ ደንጊያም እየተደባለቀ ተሠርቶበታል ። የበሩ ያንዱ መዝጊያ መጠን ቁመቱ ፲ ክንድ የጐኑ ስፋት አራት ክንድ ነው ። የቤተ ክርስቲያኑ ስፋት መቶ ክንድ (ወደ ጐን) መቶ ክንድ . . . . . . . . . ቁመቱ (ወደላይ) ግን ከ፩፻፶ ክንድ ይበልጣል ። ውስጡና ጣራው ወርቅ ለብሷል ። በውስጡ የወርቅ ምስል መልቷል። እስላሞቹ ሁሉ ሥራውን እየተመለከቱ በጣም ተደነቁ ። ሳይገቡ እውጭ የነበሩት

(1) ላሊበላ ሲል በዚህ በቤተ አምሐራ ያለ ላሊበላ እንጂ የላስታው ላሊበላ ሊሆን አይችልም ።

"ለኛም ክፈቱልንና ገብተን እንይ" ብለው ለይማም ቢጮሁ ክፈቱላቸውና ይግቡ ብሎ አዘዘ ሲከፈትም ግር ብለው ገቡ ፡፡ በዚያን ጊዜ "ከወርቁ ጥፍጥፍ (ገላከ) በቀር እያንዳንዱ እጁ ያደረሰውን ይውሰድ" ብሎ ይማም ትእዛዝ ሰጠ ፡፡ በዚያን ጊዜ ሺ የሚሆኑ እስላሞች ሺ መጥረቢያ ይዘው ወርቁንና የከበረውን ደንጊያ የተለበደውን እየፈነቀሉ እየቆራረጡ ሲያነሡ ከ፮ ሰዓት ዠምሮ እስከማታ ድረስ ጊዜ ወሰደባቸው ፡፡ ሰው ሁሉ እያንዳንዱ በወርቅ ደህና አድርጎ ከበረ ፡፡ የቀረው የወርቁ ሊሶ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር አብሮ ተቃጠለ ፡፡

ይማም በዚያው አቅራቢያ አዳር አድርጎ ሳለ ከርሱ ጋር የነበሩትን ዓረቦች "ይኸን የመሰለ የወርቅ ሐውልት ያለበት በወርቅ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን በሕንድ ወይም በሮም ግዛት አይታችሁ ታውቃላችሁን" ብሎ ቢጠይቃቸው "ይኸን የመሰለ በሮምም በሕንድም ዓይተንም አለ ሲባልም ሰምተን አናውቅም በዓለምም የለም" ብለው መለሱለት ፡፡

እቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ንጉሡ ይቀመጥባቸው የነበሩ አስደናቂ ሥራ የመላባቸው ፫ ቤቶች አሉ ፡፡ ከነዚሁ አንዱን ይማም ለራሱ ይዞ ፪ኛውን ለኤሚር አህሙሽና ለኤሚር አቡበክር ቀጢን ሰጣቸውና ፫ኛውን ግን መስጊድ አደረገው ፡፡

በበኩሉ ወዚር ኑርና ጭፍሮቹ ወደ አትሮንሰ ማርያም ሄደው ሥራውን እያዩ አደነቁ ፡፡ ወርቁን ግን አስቀድመው ክርስቲያኖቹ እንሥተው ወስደውት ኖሮ ሳያገኙ ቀሩ ፡፡ አራት መነኮሳት አገኙና ወዚር ኑር "የቤተ ክርስቲያኑ ሀብት ወዴት ነው" ብሎ ቢጠይቃቸው "ስለ እመቤታችንና ስለሃይማኖታችን እንሞታለን እንጂ አናሳያችሁም" ብለው መለሱና በዚሁ እስላሞቹ ገደሉዋቸው ፡፡ በዚሁ ጊዜ ከእስላሞቹ ወገን ፋራቃሃም አሊ በሩቁ አንድ በብረት የተዘጋ ቤት አየና ወደዚያ ሄዶ አንዱን ብረት ሰብሮ ጭንቅላቱን አስገብቶ ሲመለከት ከመሬት እንሥቶ እስከ ጣራው ድረስ ተጠቅጥቆ የተቆለለ ዕቃ ተመለከተና ወደ ወዚር ተመልሶ ይሕንኑ ነገረው ወዚሩም ከፋራቃሃም አሊ ጋር ሄዶ እቤቱ በራፍ ላይ ሲደርስ መቶ ሰው ቆጠረና "በሉ ግቡና በውስጡ የምታገኙትን ሀብት አውጡ" ብሎ አዘዛቸው ፡፡

ከዚህ በኋላ ገብተው እያንዳንዳቸው በወርቅ ፤ በብር የተጠለፈ ካባና ቀሚስ እያወጡ ያግዙ ዠመር ፡፡ ነገር ግን ዕቃው ተግዞ አላልቅ ስላለና ስለደከማቸው ቢቀመጡ ወዚር ኑር ምነው ተቀመጣችሁ ከቤት ውስጥ ዕቃው አለቀን ብሎ ቢጠይቃቸው ፤ ዕቃው እንዳለ ነው እኛ ግን ደከመን ብለው መለሱለት ፡፡ እርሱም እስካሁን ያወጣችሁት የወርቅ ካባና ቀሚስ የሐር ልብስ ብቻ ነው ፡፡ ወርቅ የለምን ብሎ ጠየቃቸውና ወርቁ ያለው ባንደኛው ጓዳ ነው ባጠገቡ ያለው ልብሱ ስለሆነ እርሱን ማጋዝ ዠመርን አሉት እነሱን ተወና ሌሎቹን ገብታችሁ የከበረውን ልብስ ማጋዝ ትታችሁ ወርቅ ብቻ አውጡ ብሎ አዘዘ ፡፡ እነሱም ገብተው ወርቁንና ብሩን እንደጽና ፣ እንደ ጻሕል (ጥዋ) ያለውን ከጥሩ ወርቅ የተሠራውን ልዩ ልዩ መሣሪያ (ንዋየ ቅድሳት) አሥር ጉልበታም ሰዎች ተሸክመው አወጡና ለወዚሩ አመጡለት ፡፡ ከዚሀ በኋላ ወዚር ኑር ቀጥራቸው ሺ የሚሆነውን ጓደኞቹን ጠራና ይኸ የኔና የይማም ፈንታ ነው እናንተ ደግሞ ግቡና የምታገኙትን ሁሉ ለየራሳ

ችሁ ውሰዱ አላቸው ። እነሱም ገብተው ወርቅም ብርም የሐር ልብስም እያገኙ ፫ም ፬ም ሸክም የሚሆን ከ፭ ሰዓት ዠምረው ለየራሳቸው ሲያግዙ አመሹ ። ማታም ሲሆን ወዚሩ ይኸው ወርቅና ልብስ ጠግባችኋል ። ይኸንንም ያገኛችሁትን በበቅሏ ችሁና በትከሻችሁ ነው እንጂ የምትሸከሙት ማጋዣ ግመል የላችሁም ከቤቱም ውስጥ ዕቃው ገና እንዳለ ነው ። ስለዚህ የቀረውን ለክርስቲያኖቹ ከመተው በቤቱ እሳት ልቀቁበት ብሎ አዘዘና ቤቱም ቤተ ክርስቲያኑም እሳት ተለቀቀበትና ተቃጥሎ አመድ ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ወደ ይማም ተመለሱና እንጉሡ ቤት ተቀምጦ አገኙት ። የራሱን ድርሻ መጠኑ የበዛ ወርቅ አቀረቡለት ። ከዚሁ መካከል በነርሱ ቋንቋ ታቦት የሚሉት እንደ ጥጃ አራት እግር ያለው (1) ክብደቱ ከሺ ወቄት የሚበልጥ ፡ ሌላ ደግሞ የሰው ሥዕል ያለበት የወርቅ መጽሐፍ ፡ የአዕዋፍና የእንስሳ መልክ ያለበት ወርቅ አራት ሰው ሊበላባቸው የሚችል ብዙ የወርቅ ሣህኖች አብረው አሉ ። ይማም ከነ ዚሁ አንዱን ለሲድ ሽሪፍ አንዱን ለገመልዲን መሐመድ ፡ አንዱን ለሲዲ መሐመድ ሀንዱል እያደላደላቸውና የቀረውን ወደ ግምጃ ቤት አስገባው ።

ሲዲ መሐመድና በሻራህ ደግሞ ወደ ቤተ ሰማያት ሄዱ ፡ ይቺን ቤተ ክርስቲያን ያሠራችው የንጉሡ የወናግ ሰገድ እናት ናት (2) እስላሞቹም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው የሚያስደንቅ ነገር ከማየት በቀር ሀብት አላገኙም ። አራት መነኮሳት አግኝተ(ISIC)ጠይቋቸውም "የንጉሡ እናት ሬሳቸው በሳጥን ሆኖ የተቀበሩበት እቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነበር የእናንተ መምጣት በተሰማ ጊዜ የንግሥቲቱንም አጽም ከርሱ ጋር የነበረውንም ወርቅ አንሥተው ወደ አምባ ወሰዱት" ብለው ነገርዋቸው ። እስላሞቹም ይኸን ከሰሙ በኋላ በቤተ ክርስቲያኑ እሳት ለቀቁበት መነኮሳቱም እያለቀሱ እነበልባሉ ውስጥ አብረው እየገቡ ተቃጠሉ ።

ከዚያ ቀጥሎ በሻራህና ሲዲ መሐመድ ወደ ደብረ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ ይቺም ቤተ ክርስቲያን በንጉሡ በአድማስ (በእደ ማርያም) በዘርዓ ያዕቆብ ልጅ የተሠራች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ናት (3) እስላሞቹም ወደ ውስጥ ገብተው ብዙ ሀብት አገኙ የንጉሡ የአድማስ (በእደ ማርያም) አጽም በውስጡ ነበር ። እስላሞቹ ከዚያው አጠገብ ብዙ የከበረ ደንጊያና ከዚሁ ጋር አንድ ቁመቱ የሰው የሚያህል የወርቅ ጥጃና ሌላውንም ወርቅ ሁሉ ሰብስበው ቤተ ክርስቲያኑን አቃጥለው ሲጨርሱ ይማም በዚያው አጠገብ ነበርና ወደ ርሱ ተመለሱ ። እርሱም ለያንዳንዳቸው ድርሻቸውን ወርቅም ልብስም አደለና የቀረውን ወደ ግምጃ ቤት አገባው ።

(1) አራት እግር ያለው የወርቅ መሠውያ ማለቱ ይሆናል እንጂ የታቦት ቅርጽ አራት እግር ያለው አይመስልም ። ወይም ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበር ነው ።

(2) ያዔ ናዖድን ባለቤት እቴጌ ናዖድ ሞገሳን ማለቱ ነው ፣

(3) እዚህ ላይ ዓረብ ፋቂህ ወይም የነገረው ሰው ተሳስቷል ። ያፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ፔሩሾ ያሳተመው በገጽ 53 - 54 ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ማሠራታቸውን ያረጋግጣል ። የአባታቸውንም ያፄ ዳዊትን አጽም ቀብረውበታል ። ምናልባት አንድ ያልተሟላ ነገር እንዳለ በእደ ማርያም በስማቸው አሟልተው ተጠርተውበት ይሆናል ።

አብድ ኢን ናስር በበኩሉ ዓዔ እስክንድር ወደ አሠራት ወደ ገነተ ጊዮርጊስ ሄዶ ደረሰ ። ንጉሡ (ልብነ ድንግል) ተሸንፎ የሸሸለት ሁለት ግምጃ ቤቶች ተማር ከው ነበር እነሱም አትግደሉን እንጂ የንጉሡ ወርቅ ብር ልብስ ፩፻ ሰው የማይችለው ሀብት ተሰብስቦ የተቀመጠበትን ሥፍራ እናሳያለን ብለውት ነበር እርሱም ወዴት አገር ነው ያለው ብሎ ቢጠይቃቸው ዋላቅ ከሚባለው አገር እተራራ ላይ እሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ብለውት ነበርና ስለዚህ አብድ ኢን ናስርን ከሁለቱ መሪዎች ጋር ወደዚያ ላከው ። እርሱም ከነጓደኞቹ ወደ ውስጥ ገብቶ ምንም ሀብት አላገኘምና ዝም ብሎ ቤተ ክርስቲያንዋን አቃጠለና ከዚያ በመሪ ዎቹ እየተመራ ዋላቅ (ወለቃ ?) ወደተባለው ቦታ የንጉሡን ሀብት ለመፈለግ አመራ ፤ በመንገድም ለሚገኘው ሰው ሁሉ እኛ ክርስቲያኖች ነን ንጉሣችንን ፍለጋ ወደ ጐጃም እንሄዳለን ይል ነበር ። ምክንያቱም ንጉሡ (ከዋስል) የሸሸው ወደ ጐጃም አቅጣጫ ስለሆነ ነው ። ከዚያ መሪው አብድ ኢን ናስርን ይዞው ደረሰን ከቤተ ክርስቲያኑ በታች በምታየው በዚህ ተራራ የንጉሡም አባት ያያቶቹም ሀብት ተሰብስቦ የተቀመጠው በዚያ ነው ብሎ አመለከተው ። ሀብቱን የሚጠብቁ አምሳ ባሮች (ዘበኞች) ነበሩ ፤ በዚሁ ቀን የጠባቂዎቹ አለቃ እናቱ ሞታ ከተራራው (ለቀብር) ወርደው ነበርና አብድ ኢን ናስር ከነጓደኞቹ ሰይፉንና ጋሻውን ይዞ ወደ ተራራው ወጥቶ እሥፍራው ሲደርስ ከአራት መነኮሳትና ከሦስት ስልብ በቀር ምንም ስላላገኘ መነኮሳቱን ገድሎ ስልቦቹን በሉ እውስጥ ያለውን ሀብት ወደ ውጭ አውጡ ብሎ አዘዛቸውና ፩፻ ሸክም የሚሆነውን እየተሻሙ ወደ ውጭ አጋዙ በወርቅ የተጠለፈ ካባና ቀሚስ ፤ የወርቅ ማህንና ጥዋ ያሁኑና የቀድሞዎቹ ነገሥታት የሚያደርጉት ብዙ የወርቅ ዘውድ የሚለብሱት ካባ በወርቅና በከበረ ደንጊያ ያጌጠ ፤ የወርቅ መታጠቂያ (ቀበቶ) ፤ የወርቅ አምባር ፡ መያዣው የወርቅ የሆነ ጩቤ ፤ የወርቅ ጥፍጥፍ ፡ አራት እግሩ በልዩ ልዩ ጌጥ አምሮ የተሠራ የወርቅ ጥጃ እንገተ፡ ሁለት ክንድ የሚሆን ፤ የወርቅ የበቅሎና የፈረስ ዕቃ ፤ ሁለመናው የወርቅ የሆነ ማህንና ስኒ ተገኘ ። የይማም ግምጃ ቤት ስለነበረ አብድ ኢን ናስር ይኸን ሁሉ ሰብስቦ በመዝገብ ጽፎ ፫ሺ ለሚሆኑት ጭፍሮቹ በያለቃቸው ደልድሎ አሸክሞ . . . . . . ወደ ይማም ተመለሰ ። ይማምና ጓደኞቹም አብድ ኢን ናስር ያመጣውን ይኸንን ሀብት እየተመለከቱ እንደዚህ ያለ ታይቶ አይታወቅም እያሉ አደነቁ ።

ከዚህ በኋላ ካባና ቀሚሱን ይማም እሦሶት ላይ ከፍሎ አንዱን ወደ ግምጃ ቤት አስገብቶ ሁለቱን ክፍል ለአብድ ኢን ናስር ሰጠው (አስረከበው ?) ። ጉጠኛና የወርቅ ዕቃ የሚሆነውን ለስጦታ እንዲሆን መደበው ። ሊመዘን የማይመቸውን ሳምባራ የሚባለውን ብዙ ወርቅ ለእስላሞቹ አከፋፈላቸው» እያለ ዓረብ ፋቂህ የቃጠሎውንና የዘረፋውን ታሪክ በዚህ ዓይነት ዝርዝር ያቀርብልናል (1) ።

የነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ቃጠሎ እንደዚህ ሆኖ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ

(1) ዓረብ ፋቂህ 307 - 316

ISIC

ላይ ተዘርዝሮ ሲገኝ በኛ በኩል ግዕዙ ታሪክ ነገሥት በአጭሩ ተጠቅሶ ነው ያለ ፈው ። ቃሉም ከአብያተ ክርስቲያናቱ ዘረፋና ቃጠሎ ጋር ተያይዞ ባጭሩ እንደ ዚህ የሚል ነው «ከ፪ ዓመት በኋላ ንጉሡ ወደ አማራ አገር ሄዶ በሐን ተቀመጠ ከዚያም በጥቅምት ፳፪ ቀን ንጉሡ ሸሸ ። በኅዳር ፰ ቀን ግራኝ መካነ ሥላሴን ፣ ደብረ ነጐድጓድን አትሮንስ ማርያምን በኅዳር ፲፪ ቀን ፣ ገነተ ጊዮርጊስን በታኅ ሣሥ ፰ ቀን ደብረ እግዚአብሔርን አቃጠላቸው ብሎ» ከዚያ ወደ ፊት ወደምናነ በው ወደ ደብረ እስጢፋኖስ (የሐይቁ) ብዝበዛ ይተላለፋል (1) ።

ባጭሩ ቢጽፈውም ወርና ቀን እየለየ የየአንዳንዱን መቃጠል ያመለከተው በሰፊው የጻፈውን የዓረቡን ጸሐፊ አተራረክ ያረጋግጣል ። ታሪክ ነገሥቱ እንደ ልማድ ሆኖ ወርና ቀን ሲጽፍ ዓመተ ምሕረት አይጨምርም ቊጥሩ ስለሚርቀው ይሁን ወይም እንደ ሌላው ሁሉ ቸልታ ይሁን አይታወቅም ። ነገር ግን የዓረቡ ጸሐ ፊና ዓረብኛውን ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት ሙሴ ረኔ ባሴት የቃጠሎውን ዓመት እንደ ኤው. ቊጥር ፲፰፻፴፩ ዓ. ም. ላይ ስላደረጉት ከዚሁ የኛን ለማግኘት ፯ ዓመት ሲቀነስ ፲፰፻፳፬ ዓ. ም. ስለሚሆን በዚሁ ዓመት በጥቅምት ፳፪ ቀን ግራኝ ዓፄ ልብነ ድንግልን ዋስል ላይ አሸንፎ ከአባረረ በኋላ በዚሁ ዓመት ፤

ሀ. መካነ ሥላሴን ፣ ደብረ ነጐድጓድን ፣ አትሮንስ ማርያምን በኅዳር ፰ ቀን ፤

ለ. ገነተ ጊዮርጊስን ኅዳር ፲፪ ቀን ፤

ሐ. ደብረ እግዚአብሔርን ታኅሣሥ ፰ ቀን አቃጥሏቸዋል ማለት ነው ። በዚያው በመካነ ሥላሴ አጠገብ ያለውን ንግሥት ናዖድ ሞገሳ ያሠሩትን የቤተ ሰማያትን ቤተ ክርስቲያን ቃጠሎ ታሪክ ነገሥቱ አያወሳውም ፣ ነገር ግን በቸልታ እንጂ የቀ ሩት ሲቃጠሉ እርሱ እንደማይተርፍ የታወቀ ነው ። የዓረቡ ጸሐፊ ቤተ ክርስቲያኑ ሲቃጠል መነኮሳቱ እያለቀሱ እነበልባሉ ውስጥ ገብተው አብረው ተቃጠሉ ያለ ውን አንብበናል ።

አንድ ከብራና የተጻፈ ደራሲው የማይታወቅ የእጅ ጽሑፍ በቤተ መጻሕፍት ቊጥር ፳፭ና ፪፻ ተሰጥቶት የተቀመጠ እንደዚህ ይላል ፣ «ንጉሥ ወደ አማራ ሄደና አቋ (ሐን) ተቀመጠ ፣ በጥቅምት ፳፰ ቀረብታ (ቀርብታ) ማርያም ራስ (ወሰን ሰገድ) ፫፻ ሊቃውንት የተከሉበትን ፣ በ፳፱ ገነተ ጊዮርጊስን ፣ በኅዳር ፩ ቀን የዓ መተ ጽዮንን ፣ ያቡነ ገብረ ማርያምን ፣ ደብረ ሕንጻታን በ፪ ያባ አንበሳን ገዳም ደብረ ድማኅን ፣ በ፫ የእጨጌን ደብር ፩፻፶ ደብተራ የነበረበትን ደብረ ገሊላን ፣ በ፬ ቀን ፬፻፶ ደብተራ የነበረበትን የንጉሡን ደብር መካነ ሥላሴን ፣ በ፰ ቀን ደብረ ነጐ ድጓድን ፣ በ፲ ቀን ደብረ ኪሩቤልን ፩፻ ደብተራ የነበረበትን በ፲፩ ቀን አትሮንስ ማርያምን በ፲፪ ጐልን ያባ ጸሎተ ሚካኤልን ፣ የእጨጌን ደብር ፣ በ፲፱ ታዕካ ነገሥ ትን ፣ በ፳፪ ገነተ ማርያምን በ፳፰ ጋስጫን ያባ ጊዮርጊስን ደብር ፣ በታኅሣሥ ፩ ቀን ደብረ ቤቴልን በ፫ ቀን ቤተ ማርያምን አቃጠለ እያለ ወደፊት የምናገኛቸውን

(1) ...... ወአመ ፳ወ፪ ለጥቅምት ተሰደ እምህየ ፣ ወአመ ፰ቱ ለኅዳር አውዓዮሙ ግራኝ በእሳት ለመካነ ሥላሴ ፣ ወደብረ ነጐድጓድ ወለአትሮንስ ማርያም ፣ ወአመ ፲ወ፪ ለኅዳር ውእየ ገነተ ጊዮ ርጊስ ፣ ወአመ ፰ ለታኅሣሥ ውእየ ደብረ እግዚአብሔር ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 92 ።

ሁሉ ይዘረዝራል ። ነገር ግን ታሪክ ነገሥቱ ያላወሳቸውን የሌሎች አብያተ ክርስቲ:
ያን ቃጠሎ ስለሚጨምር ጠቃሚነቱ ሲታይ ስለቃጠሎው ወርና ቀን ትክክል
መሆኑ አይታወቅም ። አንዳንዱ ከታሪክ ነገሥቱ ሲገጥም ሌላው ይለያያል ።
ነገር ግን ታሪክ ነገሥቱ ቢያሳጥርም የበለጠ መሠረት ያለው ነው ።

የሆነ ሆኖ ከነዚህ ከተቃጠሉት ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት በአሠራሩ ፤ በጌጡ
በሀብቱ የተደነቀውን ኢትዮጵያዊው ጸሐፊ ፩፻፶ ትክለኛ ነበረው የሚለውን የመ
ካነ ሥላሴን የሚተካከል የለም ። እርሱም ዛሬ የሚገኘው ይኸውም ማለት ከዚያ
ወዲህ የተሠራው በወረይሉ አውራጃ በለጎ ጒመራ ወረዳ ዱኪ ካቢ በሚባለው
ከተማ ነው ።

ግራኝ ከነጭፍሮቹ ወደ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ውስጧን በወር
ቅና በከበረ ደንጊያ የተሠራውን የጌጣጌጡን ፤ የሥዕሉን ፤ የሐረጉን ዓይነት እየተመ
ለካከተ ካደነቀ በኋላ ይኸን የመሰለ ሥራ በሕንድ ወይም በሮም ዓይታችሁ ታውቃ
ላችሁን ብሎ ውጊያውን ለመካፈል ከሕንድና ከቱርክ ፤ ከዓረብ አገር የመጡትን
በጠየቃቸው ጊዜ "ይኸን የመሰለ የወርቅ ሥራ በሕንድም በሮምም ዓይተንም
አለ ሲባልም ሰምተን አናውቅም" ብለው እንደመለሱለት በዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ
ላይ ተገንዝበናል ።

መቼም ሮም የሚሉት ትንሹ ሮም ተብሎ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ ስለመሠረ
ተው በርሱ ስም ቈስጥንጥንያ ተብሎ የተሠየመውንና በኋላ ቱርኮች ስጣንቡል
ያሉትን ነው እንጂ በኢጣልያ አገር የሚገኘውን ሮምን አይደለም ።

እነዚህ ወታደሮች ከያለበት ተጠራቅመው አብዛኛ ጊዜ የዘረፉ ሀብት እየሳባ
ቸው ወይም የእስላምን ሃይማኖት ለመደገፍ ሲሉ ሊዋጉ የመጡ በጦርነትና በሰ
ይፍ አመታት ወይም አመካከት የሰለጠኑ ጒበዛዝት እንጂ ከራሱ ከግራኝ ዝምሮ
ቈስጥንጥንያንና በዚች ስመ ጥር ከተማ የሚገኘውን የተደነቀውን የቅድስት ሶፍ
ያን ቤተ ክርስቲያን ያዩ አይደሉም ። እንዲያውም የሕንፃን ፤ የቅርጽን ጥበብ ለማ
መዛዘን የበቃ ችሎታና አእምሮ ያላቸው አይመስሉም ። ከነርሱ የበለጠ የተማረ
ውና የአውሮፓን የአድባራት ሕንጻ የሚያውቀው አልቫሬዝ ስለዚሁ ቤተ ክርስቲ
ያን የሰጠውን ዝቅተኛ አስተያየት እናስታውሳለን ።

በቈስጥንጥንያ ዮስጥንያኖስ ዳግማዊ (፭፻፳፯ - ፭፻፷፭) ያሠራው የቅድስት
ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን የተመረቀለት "ሰሎሞን ሆይ በለጥሁህ" ብሎ በመጮህ
የተመካበት ቤተ ክርስቲያን በማናቸውም ረገድ ዓጼ ልብነ ድንግል በቤተ አም
ሐራካሠሩት ከዚህ ከመካነ ሥላሴ ሥራ እንደሚበልጥ አይጠረጠርም (1) ። ነገር
ግን የሶፍያ ቤተ ክርስቲያን በሕንፃው ሥራ ሲበልጥ መካነ ሥላሴ ግድግዳው
ሁሉ በንጹሕ ወርቅ በብዛት የተለበደ የወርቅ ጥፍጥፍ የበዛበት በመሆኑ ብልጫ
ይኖረው ይሆናል ። እስላሞቹም ያሉት ይኸንኑ ይመስላል ።

(1) የቈስጥንጥንያው ንጉሠ ነገሥት የሶፍያን ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ያስመረቀ ለት "ሰሎሞን ሆይ
በለጥሁህ" ያለበት ምክንያት ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ያሠራው ቤተ መቅደስ በዘ
መኑ የተደነቀ ስለነበረ እሁን የበለጠ ሠራሁ ለማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፳፬

## የደብረ እግዚአብሔር መቃጠልና በሐይቅ የመካነ እስጢፋኖስ መበዝበዝ (፲፭፻ ፳፱ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲ ቀን) ከግራኝ ጋር ያሉት ዓረቦችና የውጭ ጦር ሠራዊት — የዘመኑ ጥንቆላ

ግራኝ አህመድ በሸዋ በኩል አድርጎ ወደ አገሩ ሊመለስ በአሰበበት ጊዜ እግረ መንገዱን የደብረ እግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን አቃጥሎ በሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስን ገዳም እንደአዘረፈ እንመለከታለን ። የኛ ታሪክ ነገሥት ደብረ እግዚአብሔር የሚለውን ዓረብ ፋቂህ ደብረ አዝሂር ይለዋል ። ምናልባት ባጭሩ የዘመኑ ሕዝብና ወታደር ሲጠራ የሰማውን ተከትሎ ይሆናል ። እንደዚሁም ደብረ እግዚእ ይባላል።

በቀድሞ ታሪክ ውስጥ ዮዲት የአክሱምን የነጋሢ ዘሮች በፈጀች ጊዜ ለዛሬው ሥርወ መንግሥት አባት የሆነው ድል ነአድ ወደዚች ገዳም ሸሽቶ መቀመጡ ፣ ዓፄ ይኵኖ አምላክ እመምሕሩ አባ ኢየሱስ ሞዓ ዘንድ እየተማረ ማደጉን በርሳቸውና በአቡነ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ ይኵኖ አምላክ ከነገሠ ወዲህ ደብረ ሊባኖስና ሐይቅ እስጢፋኖስ በጣም የከበሩ ገዳማት መሆናቸውን ባለፈው አመልክተናል (1) ። ከዚያ ወዲህ የእስጢፋኖስ ገዳም ያንድ ክፍል ካህናት ደቀ እስጢፋ (ደቂቀ እስጢፋኖስ) የሚባሉት ለእመቤታችንና ለጌታችን ለመስቀሉ መስገድ አይገባም በማለታቸው ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ መቀጣታቸው ተጽፏል (2) ።

የሆነ ሆኖ ይሁ የቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ያለበት የሐይቅ ደሴት በሚሾሙት መምህራን በዓቃቤ ሰዓቶቹ ምክንያት እውስጡ ከሊቃውንቱ በሚሰጠው ልዩ ልዩ ትምህርት የተነሣ በሥፍራው ማማርና ፍሬያማነት ስመ ጥር ነው ። በገዳሙ የሚሾሙት መምህራን ያቃቤ ሰዓት ደረጃ የነበራቸው ዓቃቤ ሰዓቱ በቤተ ክህነቱም በቤተ መንግሥቱም የከበረ ትልቅ ሰው እንደነበረ ባለፈው ተመልክተናል ። እንደዚሁም ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው አምባ ግሼን የነጋሢ ልጆች ይቀመጡበት እንደነበረ የሐይቅ ደሴት በፖለቲካ በጦርነት እየተያዙ የሚታሠሩበት ቦታ ስለነበረ አሁን ግራኝ ደሴቱን በሚወርበት ጊዜ አውራይ ሐርብ አራድ . . . . . . የሚባል ሡልጣን መሐመድ ካዔ ልብነ ድንግል በተዋጋ ጊዜ ተማርኮ የመጣ እዚሁ እደሴቱ ውስጥ መገኘቱን እንመለከታለን ።

የደብረ እግዚአብሔርን መቃጠልና በሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስን ገዳም መበዝበዝ ከዚያ የግራኝን ወዳገሩ መሄድና ዓመት ቆይቶ በሚያዝያ መመለሱን ለማስረዳት ታሪክ ነገሥቱ «ታኅሣሥ ፺ ቀን ደብረ እግዚአብሔር ተቃጠለ» ካለ በኋላ «ታኅሣሥ ፲ ቀን የእስጢፋኖስ ገዳም ተበዘበዘች ። ግራኝ ይኸን ካደረገና ወደ አገሩ (ሐረር) ሄዶ ዓመት ከቆየ በኋላ ተመልሶ በሚያዝያ ወር መጣ» እያለ

(1) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 1 - 2

(2) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 36

ጠቅሶት ያልፋል (1) ።

ደብረ እግዚአብሔር ሲቃጠል የእስጢፋኖስ ገዳም በመበዝበዝ ብቻ የዳነው መምህሩ ከግራኝ ጋር በመስማማታቸው ነው ። ግራኝም ሁሉን ሲያቃጥል ይኸን ገዳም ሊያተርፍ የፈቀደው በዚህ ደሴት በምርኮኝነት በኖረው በአውራይ ሐብር አራድ ምልጃ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ። ስለዚህ አሁን ከታሪክ ነገሥታችን አስበልጦ በዝርዝር የሚያስረዳንን የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከቆመበት ዠምረን እንመልከት ።

«እናንያ እሺ እመራለሁ ካለ በኋላ ይማም ዕለቱን ጉዞውን ሊዠምር አስቦ ነበር ነገር ግን የአጐቱ ልጅ አውራይ ሺሃብና ካሌድ ኤል ዋራዲ ስለሞቱ በዚህ ቀን ውሎ አድርጎ በማግሥቱ ጠሩ አራት ቀን ተጉዞ በአንጎት በኩል አድርጎ ወደ ሐይቅ ሂዶ ሠፈረ ። በሐይቁ ውስጥ አንዲት ደሴት ፤ በደሴቱም ውስጥ ቤተ ክርስ ቲያን ፤ የኮክ ፤ የሎሚ ፤ የወይን ፤ የሙዝ ፤ የዝንጅብል ሌላም ጥሩ ጥሩ የፍሬ አታክ ልት ሞልቷል ። በቤተ ክርስቲያኑም ብዙ መነኮሳት አሉ . . . . . . ።

ይማም ያጐቱን ልጅ ዘሐርቡይ መሐመድን . . . . . . ሦስት መቶ ፈረሰኛ ጨምሮ መሪውን እናንያን ይዘህ ወደ ደብረ እዝሔር (እግዚአብሔር) ሂድ ተራራው ንም ውጣ ጠላት ያያችሁ እንደሆነ ወደኔ ልካችሁ እኔ ሥፍራውን ለእግረኛና ለፈረ ሰኛ የሚመች መሆኑን መርምሬ ሳልወስን እንዳትዋጉ ብሎ አዘዘው ። ዘሐርቡይም እሺ ብሎ ተጓዘና የማታ ጸሎት በደረሰበት ሰዓት ደብረ እዝሔር ደረሰ ። በዚያም የአንጎትንና የበድል ናስርን ጦር እቤተ ክርስቲያን አጠገብ እተራራው ጫፍ መሽ ገው ተቀምጠው ተመለከተ ። እነሱን ሲያይ ኤሚር ዘሐርቡይ ከነወታደሩ እስኪ ነጋ ድረስ እቆመበት ሥፍራ አድሮ በማግሥቱ የጠላት ጦር መኖሩን ለይማም እን ዲነግሩ ፫ የፈረሰኛ መልክተኞች ላከ ። ፀሐይ በወጣ ጊዜ የጦር አለቆቹ እዚህ ለምን ዝም ብለን እንቀመጣለን ብለው ዘሐርቡይን ጠየቁት ታዲያ ምን እናድርግ ቢላ ቸው ወደ ተራራው እንውጣ አሉት ። እርሱ ግን ይማም ተዋጉ ብሎ አላዘዘም የርሱ መልስ እስኪመጣልኝ ድረስ ለጦርነት ተዘጋጅታችሁ ተቀመጡ አላቸውና እየተዘ ጋጁ ሲጠብቁ መንገድ አመልካቹ እናንያ ወደ ተራራው ወጣ ብሎ “ውጊያ ያልዠ መርናችሁ ፈርተን እይምሰላችሁ ይማም ከናንተ ያነሰ ጦር የገጠማችሁ እንደሆነ እኔ እስክመጣ ድረስ አትዋጉ” ብሎ ስላዘዘ ነው ። እደርስባችኋለሁ ብሎን እርሱን ነው የምንጠብቀው ሲመጣ ተራራውን ከነቤተ ክርስቲያኑ የሚያፈርስ መድፍ ስላለው እናንተ ሽሽታችሁ ነፍሳችሁን አድኑ ብሎ እየጮኸ ለክርስቲያኖቹ ነገራ ቸው ። . . . . . ይማም የዘሐርቡይ መልእክት ደርሶት ወደዚሁ ሥፍራ ሲደርስ አባ ራው ሲነሳ ዓይተው ክርስቲያኖቹ ሽሽት ዠመሩ ፤ እስላሞቹም እየተከተሉ ይገድ ሏቸው ዠመር የቀሩትም ተበታተኑ ። ከዚህ በኋላ እስላሞቹ ወደ ተራራው ወጡና እቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ብዙ የበረከተ ወርቅ አገኙ እያንዳንዱን አም

(1) ወአመ ፯ ለታኅሣሥ ውእየ ደብረ እግዚአብሔር ፤ ወአመ ፲፱ ለታኅሣሥ ተበርበረ መካነ እስጢ ፋኖስ ፤ ወዘንተ ገቢሮ ሖረ ብሔሮ ወነበረ ዓመተ ወተመይጠ በወርኀ ሚያዝያ . . . . ታሪክ ነገ ሥት ገጽ 328 ።

ስት ሰው ማንሣት የማይችለው አራት የወርቅ ጥጃ አገኙ (1) ። ዘሐርቡይ አራቱን የወርቅ ጥጆች አትንኩ የቀረውን ማንኛውንም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የምታገኙትን ሁሉ ለየራሳችሁ ውሰዱ ብሎ ተናግሮ ሲጨርስ ወታደሮቹ ሁሉ እየተንጋጉ ወደ ውስጥ ገቡና ግማሾቹ በሠይፍ ፣ ግማሾቹ በጨቤ ከጣራና ከየግድግዳው ላይ እየፈነቀሉ ወርቁን እያወጡ ይወስዱ ገቡ ጀመር።

ይቺን ቤተ ክርስቲያን ያሠራት ሰይፈ አርእድ የሚባል የቀድሞ ንጉሥ ነው። በተቃጠለ ጊዜ የተሠራበትን ጊዜ የሚገልጸው ፯፻፳ ዓመት (የሂጂራ) በላዩ ላይ ነበር (2) ። በላዩ ላይ ያለውም (የጨረሰው) የወርቅ ክብደቱ እንደተጻፈው ከጥጆች ከጥፍጥፉ በቀር ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ (909.999) ወቄት ወርቅ ነበር ። ሁሉንም እስላሞቹ ወስደው ከጨረሱ በኋላ እሳት ለቀው ቤተ ክርስቲያኑን አቃጠሉት ። ከዚያ ተመልሰው እተራራው ሥር ወደሚጠብቃቸው ወደ ይማም መጡና የተማረከውን የወርቅ ጥጃ አስረከቡት ።


ከዚህ በኋላ ይማም ወደሐይቅ ሄደና ሠፈረ ። በሐይቁ ውስጥ ለሚኖሩት እስረኛውን አውራይ ሐርብ አራድ ቤን ሳብር ኤዲን ኤል ሞጋሂድ የሚባለውን እናንተ ዘንድ ያለውን ላኩልኝ የሚል መላክተኛ ላከ ። ይኸም እስረኛ ሱልጣን መሐመድ ከክርስቲያኖቹ የተዋጋ ጊዜ እስላሞቹ ተሸንፈው ሲሸሹ ተማርኮ ነበር ። ንጉሡ የሱልጣን ቤተሰብ መሆኑን በተረዳ ጊዜ ወንጌልን እያስተማራችሁ ክርስቲያን አድርጉት ብሎ ከመነኮሳቱ ጋር ወደ ሐይቅ ደሴት ልኮት ይኖር ነበር ። የክርስቲያኖቹን መጽሐፍ በቃሉ እስከማወቅ ደርሶ ነበር ። ሐይቅ ከገባም ፲፮ ዓመት ሆኖታል ። ይሁን እንጂ ልቡ ከእስላምነት አልተለየም ።

ይማም ስለርሱ መላክተኛውን ልኮት ባሕሩን እየዋኘ ሄዶ ወደ መንደሩ ሲጠጋ መንደረተኛው ደንጊያ ይወረውሩበት ገባ ጀመር ። እርሱም ወደናንተ ተልኬ ነውና የምመጣው አትወርውሩብኝ አላቸው እነሱም መልክተኛ እንደሆንህ ወደ ዚህ አትጠጋ የላከኸም ያው አስማተኛው (ግራኝ) ነውና ጉዳይህን በሩቁ ንገረን አሉትና ይማም ያለውን ቢነግራቸው "ላንተም አንታዘዝ ግብርም አንከፍልህም እስረኛውንም አናስረክብም የሚቻልህን በኛ ላይ አድርግ ። ተራራ በፈረስ መውጣት እንደምትችል አውቀናል ። ይኸ ያለህበት ግን ሐይቅ ነውና ከቻልህ ግባ ብለህ ለጌታህ ንገረው" ብለው መለሱት መልክተኛውም ተመልሶ ይኸንኑ ነገረው ።

ስለዚህ ይማም ሸሪፎችን ፣ ዓረቦችን ፣ ማግረቢዎችን ፣ ማህራትን ፣ ሰብሰቦ እኛ ከመሬትና ከተራራ በቀር የባሕር ነገር አናውቅም የባሕርን ብልሃት የምታውቁ እናንተ ናችሁና ምን ይሻላል ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም ማንድና ገመድ ይቅረብልን ብለው መለሱ ። ወዲያው በይማም ትእዛዝ ግንዱም ገመዱም . . . . . ቀረበላቸው ። ከዚያ ቀጥለው ዓረቦቹ ይኸን ሠርተን የምንጨርስበት ያራት ቀን ጊዜ ይሰ

(1) የወርቅ ጥጃ የሚለው ጽላቱን ከነመንበሩ አስመስሎታል ፣ ነገር ግን እንደዚሁ የወርቅ ጥፍጥፍ ይሆናል ።

(2) ይኸን 720 የሂጅራ ዓመት ረኔ ባሴት እንደ አው ቍጥር ፲፫፻፶፮ ያደረጉት በኛ ፲፫፻፴፩ ዓ ም ይሆናል ። ዓፄ ሠይፈ አርእድ የነገሠው (፲፫፻፴፯ - ፲፫፻፷፰ ዓ ም ) የገዛበት ጊዜ ፳፰ ዓመት ነው።



የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በአሁኑ ሁኔታ ፡

ጠን ብለው ለይማም አመለከቱና ተሰጣቸው ። ከዚህ በኋላ ፫ ትልልቅ ፪ ትናንሽ ባሕር መሻገሪያ (ሊጋ) ሠርተው ጨረሱ ። በዚያን ጊዜ እስኪ እንድመለከተው አንዱን መሻገሪያ በባሕር ላይ አድርጋችሁ ሂዱበትና አሳዩኝ አላቸው ።እነሱም ትንሽን መሻገሪያ አባሕሩ ላይ አድርገው እስከ ሐይቁ መካከል ድረስ ዘልቀው ተመለሱ ፡ ይማም አካሄዳቸውን ተመለከተና የሠራችሁት ዝግ ብሎ ነው የሚሄደው በዚህ ላይ ሆናችሁ ወደ ክርስቲያኖቹ ስትሄዱ ገና ወደ ደሴቱ ስትጠጉ (ከማዝገሙ የተነሣ) ክርስቲያኖቹ በደንጊያና በቀስት ደብድበው ይፈጅዋችኋል ይልቅስ ሌላ እንዳላችሁ አሳዩን ቢላቸው ዝም አሉ በዚያን ጊዜ የበሻራህ አባት ጐ(ጀ)ሹ የሚባለው ብድግ አለና እኔ መላ አለኝ ቢል ይማም ተናገር አለው በሬ ይታረድና ቆዳው ተገፎ እንደ ስልቻ ተሰፍቶ ይነፋ በዚህም ዓይነት ብዙ ይዘጋጅና ያን ጊዜ መሻገሪያው እንደምን እንደሚሆን አሳያችኋለሁና የምለውን ብቻ አድርጉ ስላለ እንደጠየቀው ብዙ ከበሬ ቆዳ እንደ ስልቻ ያለ ተዘጋጀ ። ከዚያ በኋላ ሁሉም ደህና አድርጎ እየተነፋ አፉ እየታሠረ ሲያልቅ ይኸን የተነፋውን ስልቻ እነዚያ ከሠሩት መሻገሪያ ስር ፫ ከፊት ፣ ፫ ከማኸል ፥ ፫ ከኋላ ከታሠረበት በኋላ ሥራው ተፈጸመ ። በይማም ትእዛዝ አንዱ ይሞከር ተብሎ አባሕሩ አግብተው ሲሞክሩ ፍጥነቱ የፋላጸ ውርወራ ያህል ሆነ ይማም እኔ የፈለግሁት ይኸን ነው ብሎ ደስ አለው ይኸው ሰው የዚህን ዓይነት መሻገሪያ ያየው አበሾቹ ሊጋ የሚባለውን መሻገሪያ ሲሠሩ ነው ። ከዚህ በኋ፩፻፪ማም የማሀሪዎቹን መሪ አሕመድ ቤን ሶለይማን ኤል ማሀሪ . . . . . . የሚባለውን ተዘጋጁ አለና ቀጥሎ ማነው ከዓረቦቹ ጋር የሚገባ ብሎ ለአላህ በመሞት የሚገኘውን - የሃዲትን (1) ሽልማት እያሳሰበ ጓደኞቹን (አዳሎቹንና ሱማሌዎቹን) ጠየቀ ፤ አንድ ሁለት የሚሆኑ ተነሥተው እኛ ሕይወታችንን ለአላህ መንገድ ሸጠናል ብለው የይማምን እጅ እየመቱ ለመግባት መቁረጣቸውን ገለጹለትና ከዓረቦቹ ጋር ግማሹ ጦሩን ግማሹ ሰይፉን ግማሹ ቀስቱን እያሰናዳ ተዘጋጀ ። በዚህ ጊዜ አህመድ ቤን ሱለይማን አሁን እኩለ ቀን ነው ወደ ባሕሩ ገብተን ጉዞ የዠመርን እንደሆነ በመካከል ይጨልምና ሳንዋጋ እንቀራለን ፤ በዚህም ላይ መርከበኞቹ የረቡዕ ቀን አይሆነንም ገድ አናገኝም ይላሉ ነገር ግን ነገ ሐሙስ ስለሆነ እግዚአብሔርንና ነቢዩን ለማስደሰት ገብተን እንዋጋለን ብሎ ቢናገር ይማም ደግ ነው ነገ ይሁን ብሎ ሁሉም ወደየድንኳኑ ተመልሶ ሌሊቱን ሲጸልይ አደረ ።

ክርስቲያኖቹ በበኩላቸው እንደወፍ የሚበረውን አዲስ መሻገሪያ ሲሞክር ባዩ ጊዜ ፍርሃት አደረባቸውና እርስ በርሳቸው ምክር ይዘው እስላሞቹ እስከዛሬ ያላየነውን መሻገሪያ ሠሩ ሠሪዎቹም ዓረቦች ናቸው ። በዚህም ላይ መድፍ አላቸው የተከላከልናቸውና የተዋጋናቸው እንደሆነ በኃይል ይገቡና እኛን ገድለው ቤተ ክርስቲያናችንን ያቃጥሉታል ። ስለዚህ ሰላም ከማድረግ በቀር ለኛ የተሻለ ነገር የለንም ብለው ወሰኑ ። አባታቸው ፓትርያርኩም (መምሕረ ሐይቁ) ይኸንን የሚፈልጉትን እስረኛ እንላክላቸውና እርሱ የእርቁን ነገር ይጨርስና እነርሱም ቤተ ክርስቲ

(1) ሃዲት ከቁራን ቀጥሎ የመሐመድን ገድልና ንግግር የያዘ ጽሑፍ ነው ፡ Larousse 3 vol. ገጽ 439

ያናችንን እያቃጥሉ እኛም ሀብቱን በፈቃዳችን እንስጥ ብሎ ተናገረና በዚሁ መሠረት እስረኛውን ጠሩትና ይኸንኑ ነገሩትና እሺ አለ ። ከዚያ ሁለት ሰው በሌሊት እስላሞቹ ሳያዩ እጠረፍ በታንኳ አድርሳችሁት ተመለሱ ተብለው የታዘዙት ሁለት ሰዎች እጠረፍ ሌሊት አምጥተው ለቀቁትና ታንኳቸውን ይዘው ተመለሱ ።

ጧት ይማም ጸሎቱን አድርሶ ሲጨርስ ወደ ድንኳኑ ተመልሶ ምሳ አምሮት ለመብላት አብሳማ ኑርን አስጠራው ። አብሳማ ኑር ወደ ይማም ለመምጣት ግማሽ መንገድ ሲቀረው ክርስቲያኖቹ የላኩትን እስረኛ እመንገድ አገኘና ማነህ አንተ ብሎ ቢጠይቀው እኔ ሐርብ አራድ ቤን እውራይ ሳብር ኤዲን ነኝ የሐይቅ መንደረተኞች ወደ ይማም ልከውኝ መምጣቴ ነው ብሎ መለሰለት ከዚያ አብሳማ ኑር ወደ ድንኳኑ ገብቶ ለይማም ነገሩን ቢገልጽለት ወዴት አለ ስለርሱ ነበር ከዚህ በፊት ወደ ሐይቁ ውስጥ መላክተኛ ልኬ የነበረው አለ ። አብሳማ ኑርም እደጅ ነው ያለው ስላለ ይግባ ተባለና ወደ ውስጥ ገባና ይማም በዚህ በግዞት አገር ሰውነቱ ተለዋውጦ እየውና አዝኖ አለቀሰለት ። ሐርብ አራድም አብሮ አለቀሰ ፤ ስንት ዘመን በዚች ደሴት ኖርህ ብሎ ቢጠይቀው ፲፰ ዓመት ሆነኝ ። አሁን ግን ዓረቦቹ የሠሩትን መሻገሪያ ክርስቲያኖቹ ባዩ ጊዜ ፈሩና እርሱም አይግደለን ቤተ ክርስቲያናችንንም አያቃጥል እኛም ሀብቱን እናስረክብ ብለው እንድማልዳቸው ላኩኝ ብሎ መለሰለት ። ይኸን ከሰማ በኋላ ይማም አጠገቡ ላሉት ጓደኞቹ ለነአቡበከር ቀጢን ፤ ለነወዚር ሞጃሂድ . . . . . . ምን ይ[illegible]ስላችኋል ይኸ ነገር ብሎ ጠየቃቸው ። እነሱም ክርስቲያኖች ለማታለል ይሆናል እንጂ ሀብቱን አያስረክቡም ብለው መለሱ ። ይማም ግን እንደዚህ ያለውን ንግግራችሁን ተዉኝ ለኛ የዚህ የእሥረኛው መለቀቅ ብቻ ተራራ ከሚያህል ወርቅ ይበልጥብናል አለና ወዲያው ሐርብ አራድን መልካም ነው እንዳላችሁት ይፈጸም ብለህ ተመልሰህ ንገራቸው አለውና ተመልሶ በታንኳ ወደ ደሴቱ ሄደ ። በዚያም ክርስቲያኖቹን ሰበሰበና ይኸውና እናንተም እንዳትሞቱ ቤተ ክርስቲያኑም እንዳይነካ ከይማም ቃል ተቀብያለሁ ። ይኸም የሚፈጸመው እናንተ በሰጣችሁት ተስፋ የታመናችሁ እንደሆነ ነው ። ስለዚህ ፓትርያርኩ (መምህሩ) ሄደው የሰላሙን ነገር ይጨርሱ ብሎ ነገራቸውና እርሱ ተመልሶ ወደ ይማም መጣ ። ይማም ወደ ጠረፉ መጥቶ ቆመ ፤ የዓረብ የእግረኛ ጦር ማህሪትና ማግረብ የሚባሉት ሸሪፎችም ሸሪፍ ኑር ና ሸሪፍ መሐመድ ሐንዲልም ተሰልፈው ኰልኩለው ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ ፓትርያርኩ ከቤተ ክርስቲያኑ (ከገዳሙ) ወጥቶ በታንኳ ተሻፈረና እይማም ዘንድ ደርሶ መሬቱን ሊስም ፈለገ ይማም ግን ምስኪን እሰው ፊት አትስገድ ብሎ ከለከለውና ይልቅስ የመጣህበትን ተናገር አለው ሰዎቹን እንዳታጠፋ ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዳታቃጥል ቀሳውስቱ ሁሉ ይለምኑሃል ቢል ደህና ነው እናንተም የቤተ ክርስቲያኑንም ሌላውንም ሀብት ካልደበቃችሁ እኛም አንነካም ብሎ መለሰለት እርሱም እሺ ሁሉንም ወደ ደሴቱ ተመልሼ ሄጄ እመጣለሁ አለ ። እስላሞቹ ግን . . . ባንተ እምነት የለንም የኛ ጓደኞች ካንተ ጋር ወደ ደሴቱ ገብተው ያምጡ አሉት ። እርሱም እስላሞቹ ከኔ ጋር ወደ ደሴቱ እንዲገቡ ግዴታ ከሆነ ጉዳት እንዳያደርጉ ይታዘዙ

ልኝ ብሎ አመለከተ ይማምም እኔ ተስፋ ከሰጠሁ ማንም ቃሌን አልፎ የሚነካብህ የለም አለውና ደስ አሰኘው ። ከዚያ ይማም የዓረብን አገር ወታደሮች ማሀረትንና ማግረብን ሸሪፎቹን ሰጠውና መሐመድ ዘሐርቡይን እንደዚህ አለው አንተው ራስህ ከፓትርያርኩ ጋር ወደ ደሴቱ ግባ ቤተ ክርስቲያኑን አታቃጥል መነኰሳቱንም አትግደል ። ነገር ግን በደሴቱ ውስጥ ያለውን ሀብት አንድም ሳታስቀር ሁሉንም ይዘህ ና . . . . . አለውና ዘሐርቡይ በታንኳ ሆኖ ወደ ደሴቱ ገባና ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ወርቅ በጉድጓድና በጓዳ ውስጥ አሥር ሰው የማያነሣው የወርቅና የብር መስቀል ቍጥሩ የበረከተ ሰንሰለቱ የወርቅ የሆነ ብዙ የሻማ ማብሪያ የወርቅ መጻሕፍት ብራናውና ጥራዙ ያማረ በወርቅ የተሠራ ዕቃ (1) ። እያንዳንዱ እስላም ፫፻ ወቄት የሚሆን ወርቅ አገኘ ፫ ሰው አጥግቦ ሊያበላ የሚችል የወርቅ ማህን (ብርት ወይስ ጻሕል) ። ትልቅ ቁልል የሆነ የሐር ልብስ . . . . . በመሰብሰብ ዘሐርቡይ ሌሊቱን እዚያው እደሴቱ አደረ ።

በማግሥቱም ፲፭ ሰው በሚይዘው መሻገሪያ ወርቅ ፣ ብር ፣ ልብስ ሞልቶ ከኋላ ፪ ፤ ከፊት ፫ ሰው ብቻ ጨምሮ ፫ መሻገሪያ ሞልቶ ለይማም ላከለትና ይኸ ሁሉ ሀብት እፊቱ ተዘረገፈ ። ይማም ባየ ጊዜ ተደንቆ ባሁኑ ሀብት ከዚህ በፊት ያየውን ሁሉ ዘነጋው ። መሻገሪያዎቹም ፫ ጊዜ ተመላልሰው የቀረውን አግዘው ጨረሱና ወደ ደሴታቸው ተመለሱ ። ዘሐርቡይ እደሴቱ በሄደ በሁለተኛው ቀን ማታ መጥቶ ከይማም [illegible]ኛና እሠፈሩ አደረ ። በማግሥቱም ይማም አስጠራውና ክፍያ ተዠመረ አንዱን ክፍል ለዘሐርቡይና ለባሕር ወታደሮች ፤ አንዱን ክፍል ለዓረቦች ሰጠና የቀረውን ለእስላም ወታደር እንዲከፋፈለው አደረገ » (2) ።

በዚህ በያዝነው ምዕራፍ ውስጥ በሁሉ ቦታ እየመራ ግራኝን የሚያገለግለው ከሐዲው አናንያ አሁንም ጌታው አውራይ ኡስማን ከሞተ ወዲህ አገልግሎቱን ለወገኖቹ ጠላት ሳያቋርጥ እንደሚቀጥል እንረዳለን ። በደብረ እግዚአብሔር ተራራ ላይ ቤተ ክርስቲያኑን ሊከላከሉ የተዘጋጁትን ወታደሮች እስካሁን ያልወጋናችሁ ፈርተን አይምሰላችሁ ይማምን (ግራኝን) ስንጠብቅ ነው እርሱ ሲመጣ ቤተ ክርስቲያኑን ከነተራራው በመድፍ ሲያፈርሰው እናንተ እንዳታልቁ ብሎ በሚያውቀው ባገሩ ቋንቋ ያገሩን ሰዎች ልብ እያሸበረ የግራኝን ወረራ በዘዴ ጭምር አቃንቶለታል ። ሽሹ ማለቱም የግራኝን ጦር ከውጊያ ለማዳን ሀብቱን እንደልብ ለማስዘረፍ እንጂ ለወገኖቹ ሕይወት ሳስቶ አይደለም ።

አዝማች ሃይቢም በሌላው የጦር ግንባር ደንበኛ የጠላት መሣሪያ መሪ መሆኑን ባለፈው ተገንዝበናል ። እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች ከታማኝ ሕዝብ መካከል አልፎ አልፎ በየዘመኑ ይገኛሉ ። በኢጣልያ ጦርነት በዓድዋም በማይጨውም ጊዜ አገሪቱ በተያዘችበት የ፭ ዓመት ዘመን አናንያን ፣ ሐይቢን የመሰሉት አልጠፉም ። ይኸም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን አገርንና ወገንን በጦርነትም በሰላምም

(1) ጽላቱን ማለቱ ይሆን ፡
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 326 - 337

ጊዜ የሚከዳ ከማናቸውም ክፍለ አገር አይጠፋምና ሊያሳዝን እንጂ ሊያስደንቅ አይችልም ።

በግራኝ ጦርነት ላይ ብዙ ጊዜ የባሕር ወታደሮች ፣ ዓረቦች ፣ ማግረብ ፣ ማህሪ የሚል ቃል ይገኛል ። እንደዚሁም ዓፄ ልብነ ድንግል የግራኝ ጦርነት እንደተዠመረ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ ደብዳቤ ሲጽፉ "በወሰኔ ላይ አንድ የእስላም ንጉሥ (ግራኝ ወይም የሐረር ሱልጣን አቡበከር) . . . . . ከሕንድ ፣ ከፋርስ ፣ ከዓረብ ፣ ከግብፅ ነገሥታት ጋር ቃል ኪዳን እያደረገ ከነርሱ በሚያገኘው እርዳታ እኔን ያላንዳች ክርስቲያን ንጉሥ እርዳታ እየወጋ በጣም የሚያናድድ ትልቅ ጦርነት አድርጎብኛል" ሲሉ የጻፉትን ወደፊት እናነባለን ። እንደዚሁም ግራኝ መካነ ሥላሴን ያቃጠለ ጊዜ ስለሥራው እየተደነቀ በአጠገቡ ያሉትን የውጭ አገር ወታደሮች እስቲ እንደዚህ ያለ ሥራ በሕንድ ፣ በፋርስ ፣ በሮም (በቁስጥንጥንያ) ዓይታችሁ ታውቃላችሁን ብሎ የጠየቃቸው እነዚህኑ ከፋርስ ፣ ከሕንድ ፣ ከዓረብ ፣ ከግብፅ ፣ ከማህሪና ከማግረብ ጦርነቱን ለመካፈል የመጡትን መሆኑ ጥርጥር የለውም ።

ዓረቦች ሲል ማናቸውንም የዓረብ ተወላጅ ለማለት ሳይሆን አይቀርም ፣ ማህሪ ወይም ማህራ በደቡብ ዓረብ የሚኖሩ ቋንቋቸው ከጥንቱ ሄሚያሪት የመነጨ ከአሁኑ ዓረብ ጋር የተለየ ነው ። የጥንቱ የሄሚያሪት ፊደልና ቋንቋ ለኛም ለግዕዙ ቋንቋና ለፊደላችን አባት ነው ። ይኸም የሆነው ነገደ ዮቅጣን የተባሉት ከዚሁ ከደቡብ አገር ኤርትራን ተሻግረው መጥተው ስለ ተቀመጡ ነው ። ይኸንንም በአክሱም መንግሥት ታሪክ ውስጥ በሰፊው ከነፊደሉ አመልክተናልና አንመለስበትም።

ISIC

ማግረብ የሚባለው ማሮክ ፣ አልዠር ፣ ቱኒዚ ፣ ሊቢያ ፣ ያሉበት ሰሜን አፍሪካ ነው ፣ ማግረብ ማለትም ምዕራብ ማለት ነው ። ስለዚህ ከዚሁ ከሰሜን አፍሪካ ተሰብስበው የመጡ ወታደሮች ጦርነቱን ተካፍለዋል ማለት ነው ። ከማግረብና ከማህሪ ከፋርስና ከሕንድ ነገዶች ውስጥ ተመርጠው መጥተው ግራኝ አህመድ በተዋጋበት ሥፍራ ሁሉ አምርር አቶማን (የቱርክ የቁሣር ግዛት) የቀናበትን ጥሩ ጥሩ የጦር መሣሪያና መድፍ ይዘው መጥተው አስፈሪውን አምባና በጠባዩ ምሽግነት ያለውን የመከላከያ ሥፍራ ሁሉ በመድፍ በማፈራረስ እየተዋጉ በብዙ ረድተውታል ። እርሱም ከየገዳሙና ከየቤተ ክርስቲያኑ ነገሥታቱ በስጦታ ፣ በስለት አድልበውት የነበረውን የብርና የወርቅ ፣ የልብስ ሀብት እየሰጠ አክብሯቸዋል ። ከነዚህ ከማህሪና ከማግረብ ጋር ጽሑፉ ለብቻ የባሕር ሰዎች እያለ የሚጠራቸው አሉ ። እነዚህ የባሕር ሰዎች የሚላቸው ምናልባት ከሰፊው ከቱርክ ግዛት ተሰብስበው ከባሕር ማዶ የመጡ ቱርኮችና ፈረንጆች ያሉበት የነጭ የጦር ሠራዊትን ይሆናል ። በዚህ ጊዜ የቱርክ መንግሥት የመካከለኛው ምሥራቅንና ሰሜን አፍሪካን ከመግዛቱ በቀር ግሪኮች ፣ ቡልጋሮች ዛሬ ዩጎስላቪያ የሚባሉት የሴርቦ - ክሮአት ሕዝቦች አርመኖች ፣ ሩማንያዎች፣ ሁንጋሪያዎች ያንጊዜ የርሱ ተገዥዎች ናቸው ። በዚህ ምክንያት ከዚሁ ሰፊ ግዛት ታዘው ወይም ለሀብት ፍለጋ በገንዘብ እየተቀጠሩ በፈቃዳቸው የሚዋጉትን ፈረንጆቹን ወይም ቱርኮቹን ብቻ ይሁን በትክክል

አይታወቅም ። የግብፅና የቱርክ ሱልጣኖች የፖርቱጋልና የኢትዮጵያ መንግሥት ከ፲፭፻ ዓ.ም. ዠምሮ የወጠኑትን ዝምድና በሥጋት እንደሚመለከቱትና ይኸንኑም ለመደምሰስ እንደሚያስቡ የታወቀ ነው ። የሕንድ አገረ ገዥ ሎፒዝ ሱአሬዝ ብዙ መርከብ ይዞ እንደ እው ቊጥር ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. ምጥዋ ድረስ መጥቶ የቱርኮቹንና የግብጾቹን ጦር አሸንፎ አገሩን ከያዘ በኋላ ሮድሪግ ደሊማን ወዳዤ ልብነ ድንግል መላኩ በግብጽና በዓረቦች አገር   የታወቀ ነገር ስለሆነ ግራኝ አህመድን ለመር ዳት የዓፄ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለመጣል ምናልባትም ከባልካን ጭምር እየ ተመለመለ የሚሄደውን ጦር የበላይም የበታችም ባለሥልጣኖች ስለሚደግፉት በአሁኑ ሰዓት ባለፈው እንደተባለው የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ የባሕር ሰዎች የሚላ ቸው ሃይማኖታቸው ምንም ይሁን ነገር ግን ከባሕር ማዶ ከቱርክና ከባልካን የመ ጡትን ይሁን ወይም ቱርኮቹን ብቻ ማለቱ ይሁን አይታወቅም ።

ስለዚህ ባጭሩ የምንመለከተው ግን የነዚህ ከውጭ ተሰብስበው የመጡት ወታደሮች የእጅ ብልሃትና የያዙት የመሣሪያ ጥራት ፤ የግራኝ ጥብቅና ብልህ መሪ ነት ፤ ቊጥሩ ከበረከተው ከአገሩ ተወላጅ ከሱማሌው ከአዳሉ ከሌላውም ነገድ ጋር ተባብሮ የቱርኮች የግብጾች የበላይ ጠባቂነትና ደጋፊነት እስላሙን ግራኝን አሸ ናፊ ክርስቲያኑን ዓፄ ልብነ ድንግልን ተሸናፊ አድርጐ አሳይቶናል ። ዓፄ ልብነ ድንግልን ሊረዳ ተሰፋ የሰጠውና ዝምድናውን የቀሰቀሰው በቀሰቀሰውም ዝምድና ይኸን የጦርነት እሳት ለማቀጣጠል ተጨማሪ ምክንያት የሆነው የፖርቱጋል መን ግሥት ባሁኑ ሰዓት ድምፁ ስለጠፋ ልብነ ድንግል ተስፋ ቢስና ብቸኛ ሆነው የጦር ነቱ ወላፈን ከደዋሮ ዠምሮ እያቃጠለ እስከ ቤተ አምሐራ ካሳደዳቸው በኋላ ከዚ ያም አባርሮ እነሆ በግሼን አልፈው ወደ ደላንታ እንዲሸሹ አድርጓቸዋል ።

ይኸን ዝርዝር የፖለቲካና የወታደርነት ሁኔታ ለመመልከት ያዳገታቸው የኛ ዎቹ ታሪክ ነገሥቱን ያዘጋጁት አንድም ሥፍራ ላይ ይኸን ሁሉ የውጭ እርዳታ አላ ነሡትም ። በነርሱ ዘንድ የዚህ የግራኝ ጦር የማይደፈረውን ቊጥሩ የበረከተውን የኢትዮጵያ ጦር ለማሸነፍ ኃያላኑን የጦር አለቆች እነራስ እስላም ሰገድን ፤ እነራስ ወሰን ሰገድን እመግደል ገናናውን ንጉሠ ነገሥት እማሳደድ የደረሰው በምን ምክን ያት ነው እያሉ በአሳባቸው ከተጠበቡ በኋላ መደምደሚያውን የግራኝን ድል አድራጊነት በአስማት ላይ ላከውታል ። በዚህ ምክንያት ከዚህ በፊት እንዳልነው ግራኝ አሕመድ ብለን የምንጠራውን ያን ጊዜ አስማተኛው የሚል የቅጽል ስም ጨምረውለት እንደነበረ በዋስል ጦርነት ላይ ከዛፍ እየቆረጠ በሚዋጋበት በትር አስማትእየደገመ ያሸንፋል ወይም የሚዋጋበት በትር ያፍዝ ያደንግዝ አለው ማለታ ቸውን ባለፈው ያነበብነውን አሁንም የሐይቅ ገዳም መነኮሳት ከግራኝ ወደነርሱ የተላከው መላክተኛ እየዋኘ ወደነርሱ በቀረበ ጊዜ «የላከህ አስማተኛው መሆኑን እናውቃለንና ጉዳይህን በሩቁ ተናገር» ማለታቸው የሁሉም አስተያየት በግራኝ አስማተኛነት ላይ መሆኑን እንገነዘባለን ።

አስማተኛ ነው ለተባለው ከዚህ ቀደም እንዳልነው መቼም በዚያን ጊዜ (አሁ ንም ጭምር) የክርስቲያኖቹም የእስላሞቹም መሪዎች ሲዋጉ ሲሉ የትኛው ቀን

እንደሚሆናቸው እስላሞቹ ሸካቸውን ፤ ክርስቲያኖቹ ጠንቋይ ፤ ደብተራ ወይም የበቃ መነኩሴና ባሕታዊ እንደሚጠይቁ የታወቀ ነው ። ሟቹ ራስ ወሰን ሰገድ ለውጊያ ቅዳሜን መርጦ እንደነበረ ይታወሰናል ። እነዚህ ወደ ደሴቱ ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ሊገቡ ያሰቡት ዓረቦች የረቡዕ ቀን መጥፎ ሐሙስ ጥሩ ነው ማለታቸውን ታሪካዊው ጸሐፍ ሲገልጽልን እስከ ዛሬ በኛም ዘንድ ሐሙስ የቀን ቅዱስ የምንለው በሁለታችንም ዘንድ ስሜቱ ከቀድሞ ዝምሮ የመጣ መሆኑ ትዝ ሊለን ይገባል ። የግራኝ አሕመድ የማዕርግ ስሙ ይማም ከሱልጣን ያነሰ ነው። ነገር ግን እርሱ ባሁኑ ሰዓት ከሱልጣን የበለጠ ሥልጣንና ችሎታ ሲኖረው ዝቅተኛውን የይማምነትን ደረጃ እስከመጨረሻ ይዞ የዘለቀበት ምክንያት ገና ከሥር ከመነሻው ላይ ያገሩ ሸኮች ይማም እንጂ ሱልጣን አይባል በማናቸውም ነገር አበሻን ሊያሸንፍ ፤ ሊገዛ የሚችለው በዚህ ስም ብቻ ነው ብለው ስለአዘዙ ነው ። ይኸም ከንግርትና ከጥንቆላ ጋር የተያያዘ ውሳኔ መሆኑ ነው ።

ስለዚህ ራሱ አስማተኛ ጠንቋይ አለ መሆኑን ዓረብ ፋቂህ ክዷል (1) ። በሌላም እስካሁን ባየሁት ጽሑፍ ግራኝን አስማተኛ ነው የሚል አላጋጠመኝም ። ነገር ግን በውስጡ ያሉት ሼኮች ከቢሮች ጥንቆላም ሟርትም እያደረጉ የውጊያ የጉዞ ቀንና ሰዓት እየመረጡ ሲነግሩት እርሱም እንደዘመኑ መሪ አሳባቸውን እየተቀበለ መፈጸሙ የታወቀ ነው ። ቀን በማጋደሉ ድርጅትና አስተዳደር ከመሠረቱ በመበላሸቱ አልረዳም እንጂ ይኸን በመሰለ በቀን መረጣና በአምልኮ ጉዳይ ልብነ ድንግልም ሳይጠቀሙ እንደማይቀሩ የታወቀ ነው ።

ደብረ እግዚአብሔር ተዘርፎ የተቃጠለበት ታኅሣሥ ፳ ቀን መካነ እስጢፋኖስ ሳይቃጠል የተበዘበዘበት ታኅሣሥ ፲ ቀን መሆኑን ታሪከ ነገሥታችን ሲነግረን ዓመተ ምሕረቱን ትቶታል ። ነገር ግን ሊቁ ሙሴ ረኔ ባሴት የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊ ሲተረጉሙ በገጽ ፫፻፶፫ ግራኝ ወደቤተ አምሐራ ሲዘምት አዶሌ ሸዋ ቀርቶ አገር ሲያቀና ሁለቱ የተለያዩበትን የሰባት ወር ጊዜ እንደ ኤው. ቍጥር ሐምሌ - ነሐሴ ፲፭፻፴፩ እስከ ጥር - የካቲት ፲፭፻፴፪ አድርገውታል ስለዚህ በኛ ሲታሰብ ዓመተ ምሕረቱ ፲፭፻፳፬ ይሆንና ወሩም ያው ታሪከ ነገሥታችን የጠቀሰው የደብረ እግዚአብሔር ቃጠሎ ታኅሣሥ ፳ ቀን የመካነ እስጢፋኖስ መበዝበዝ ታኅሣሥ ፲ ቀን መሆኑ ነው ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 302 - 303

## ምዕራፍ ፳፮
## ስለ እምባ ግሼንና በላዩ ላይ ስላሉት መሣፍንት

የዛሬም የጥንትም ባለሥልጣኖች ነፍስ የገደለውንም የሠረቀውንም ማናቸውንም ወንጀለኛ የቆየ ደንብና ሕግ ተከትለው በብዙ ዓይነት ደረጃውን እየለያዩ ይቀጣሉ። ጥርስ በጥርስ የሚለው ኦሪታዊው ሕግም ከሌላው ዝርዝር ሕግ ጋር በክርስቲያንና በእስላም አገሮች ተወርሶ እስከ ብዙ ዘመን ሲሠራበት ኖሮአል ። በኢትዮጵያም የፖለቲካ እስረኛ ፤ ከጦርነት ላይ የተያዘ ምርኮኛ ፤ አስተዳደርን የተቃወመ ፤ ንጉሥን ያማ ፤ ከደንበኛው የተዋሕዶ ሃይማኖት የወጣውን መናፍቅ ፤ በየአገሩ ያሉ ደሴቶችና ሰውን እንደልብ የማያስወጡት ተራራዎች የነዚህ ሁሉ መጥፎ አስተናጋጆች ሆነው ኖረዋል ። ከነዚህ የበለጠ ደግሞ የሚያሳዝኑት ምንም ወንጀልና ጥፋት ሳይገኝባቸው ያለ ፈቃዳቸው ካንድ ንጉሥ ወይም ካንድ መስፍን በመወለዳቸው ብቻ ይኸው ራሱ እንደ ጥፋት ተቆጥሮባቸው በየደሴቱ ፤ በየተራራው የግዞት ቦታ ዕድሜያቸውን የሚፈጁት ናቸው ። አደገኛም ነው የሚሉ ጥርጣሬ እንዳለ እግረ ሙቅ በግሩ ሰንሰለት በክንዱ መሸከም አለበት ። ዙፋን ሊቀናቀን የሚችል አንዱ መስፍን መጠነኛ ጥፋት የተገኘበት እንደሆነ አካሉ የጐደለ መንገሥ አይችልም ስለሚባል እጁ ወይም እግሩ ተቆርጦ ዓይኑ ፈሶ አካለ ጐደሎ ሆኖ ይቀመጣል ።

አንድ ንጉሥ በተለይ በመካከለኛው ዘመን ለፖለቲካው ወይም ለሥጋው ፍትወት ሲል እስላም እንደሆነ በሚስትነት ክርስቲያንም እንደሆነ እንዷን አግብቶ የቀሩትን በዕቁባትነት ስም ያስቀምጣቸዋል ። ከነዚህ ብዙ ልጆች ሲወለዱ ከመካከላቸው አንዱ አባቱ የመረጠው ወይም መኳንንት የፈቀዱለት ሲነግሥ ነጋሚው ያልነገሡትን ይጠላል ፤ ያስራል ። ካላሠራቸውም እነዚያ የርሱም ደም የኛም ደም ካንድ ግንድ የመነጨ ስለሆነ ለመንገሥ ምን የሚከለክለን ነገር አለ በማለት ወገን ይዘው ሊነሡ ይችላሉ ። አንዳንድ በሹመት ያልተደሰተም ቀንደኛ እነሱን መሣሪያ አድርጎ በመንግሥት ላይ ይነሣል ። በዚህ መካከል ከሁለቱም ወገን ያው መከረኛ ተከታይ ሕዝብ ያልቃል ።

ይኸን ሁኔታ ለማስቀረት እንደምንም ብሎ መንገሥ የቻለው ንጉሥ የጨከነው የሚፈራቸውን ወንድሞቹን ይዞ ይገድላል ፤ የራራው ያስራል ። እንደዚህ ያለውም መጥፎ ልማድ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም ። ዳግማዊ መሐመድ የሚባለው ቁስጥንጥንያን እንደ አው. ቀ. በ፲፭፻፶፫ ዓ. ም. ድል አድርጎ የያዘው የቱርክ ሱልጣን ከልጆቹ ከልጅ ልጆቹ አንዱ ሥልጣን ሲይዝ ዓለም ሁሉ እረፍት ያገኝ ዘንድ ወንድሞቹን እንዲገድል ኡላማዎቹ (የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች) ፈቅደውለታል የሚል ትእዛዝ (ካኑን) አውጆ ነበር (1) ።

በኛም በኢትዮጵያ ዘንድ በዙፋን የተቀመጠው ንጉሥ በመስፍኑ ወንድሙ ላይ የንቅናቄ መንፈስ ሲያይ ወይም በጥርጣሬ መግደሉ ማስገደሉ የማይቀር ነው ።

(1) Soliman le magnifique F. DOWNEY............ ገጽ 187 - 188

ግን ግድያው እንኳን እንደ ብርቅ ቢሆን እሥር ማስቀመጡ ከጥንት ዝምሮ የተለመደ ነው ። በአክሱሞች ዘመን ደብረ ዳሞ በዚህ በመካከለኛው ዘመን አምባ ግሼን (ቤተ አምሐራ) አምባ ሠነይት (ተምቤን) ከዚያም ወዲህ መቅደላ ፤ እፍ ቀራ ፤ አንኮበር ፤ ዝቋላ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ የነጋሢና የተጠርጣሪ የግዞት ቦታዎች ናቸው ።

በዚህ በመካከለኛው ዘመን ግን ከሁሉ የበለጠ የነገሥታት ልጆች የግዞት ሥፍራ በመሆን ስመ ጥር የሆነው በዚሁ በቤተ አምሐራ የሚገኘው የግሼን አምባ ነው ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ባንድ ሚስት መወሰንን የዠመሩት እኚህ መከረኛው ንጉሥ ዓፄ ልብነ ድንግል ናቸው (1) ። ከርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታት ብዙ ሚስቶች ያገቡ እንደነበረ ራሱ ዜና መዋዕላቸው በየቦታው ያስረዳል ። ዠግናው ንጉሠ ነገሥታችን ዓምደ ጽዮን ታላቂቱ ንግሥት (ጽዮን መንግሣ) ታናሺቱ ንግሥት የሚባሉ ሚስቶች ነበሩት ። እንደ ዛሬ ከአዳሎቹ ጋር ሲዋጋ እኋላ ሆነው ሁለቱም ስለሕይወቱ ይላቀሱለት ነበር (2) ። በዚህም ላይ ያልወለደችኝን ያባቴን ሚስት አገባለሁ ብሎ ከእጨጌ ፊልጶስ የነበረው ጠብ የታወቀ ነው ። ከርሱ ወዲህ ያሉት እነዘርዓ ያዕቆብ ፤ እነበዕደ ማርያም ከሌሎቹ ዕቁባቶች በቀር የታወቁ የግራ ባለቤት ፤ የቀኝ ባለቤት የሚባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩዋቸው (3) ። በ፲፭፻፳ - ፳፯ ዓ. ም. እንደ አው. ቍጥር ባዔ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት የነበረው አልቫሬጽ ያፄ ልብነ ድንግል አባት ዓፄ ናዖድ አምስት ሚስቶች እንደነበሩዋቸው በወሬ የሰማውን በመጽሐፉ ጽፎታል (4) ።

መልክና የደም ግባታቸው ያቋቋማቸው ቅርጽ የተለያየውን ሴቶች በብዛት በያለበት በሚስትና በዕቁባት ስም ማስቀመጥ የሥጋ ፈቃድን ለማስደሰት መሆኑ አይጠረጠርም ። በዚሁ ጐን የምንመለከተው በዘመኑ የነበረውን የፖለቲካ ጥቅም ነው ። ነጋሢው ከብዙ የነገድ ባላባቶች ጋር ሲጋባ ምንም ከብዙ ሴቶች የተወለዱት ልጆች በኋላ ዙፋን ለኔ ይገባል እያሉ ባገር ላይ ሁከት መፍጠራቸው ባይካድ ለጊዜው ግን በሥልጣን ላይ ላለው ንጉሥ አገዛዙን ያጸናለታል ።

በዚህ ምክንያት ከልብነ ድንግል በፊት የነበሩት ነገሥታት ከሐድያ ፤ ከደዋሮ የባላባት ልጆች ጋር መጋባታቸው ለመንግሥታቸው ጸጥታና ሰላም በመሻት መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ነገር ግን ከብዙ ሴቶች ከተወለዱት ወንዶች ልጆች ውስጥ ሲያድጉ አንዳንዶቹ እንደ አቤሴሎም ዙፋንን ካባታቸው ለመቀማት አንዳንዶቹም ነጋሢው አባት በሞተ ጊዜ እኔ ልንገሥ ፤ እኔ ልግዛ እየተባባሉ በየወገናቸው ተነሥተው ሲዋጉ ያገር ጸጥታ እየደፈረሰ ብዙ ሰው ማለቁ ንጉሡም የቤተ ክህነቱና የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ስለተሰማቸው አንዱ የተመረጠው ከነ

(1) ታሪከ ነገሥት ገጽ 96 ። አልቫሬጽ . . . . . ምዕ. 49 ገጽ 110

(2) Hist. de guerre d'Amde Syon…ገጽ 388 - 389

(3) የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. 29

(4) አልቫሬጽ ምዕ. 113 ገጽ 299

ገሥ በኋላ የቀሩትን ሰብስቦ ባንድ በተለየ ሥፍራ ማስቀመጥ የተሻለ ዘዴ መሆኑን ተገንዝበው ገና በፊት የዚህ ዓይነት ልማድ ከዠመረ መቆየቱን ካዬ ይኩኖ አም ላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በሚባለው መጽሐፍ በምዕራፍ ፶፱ በዓፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ላይ ተመልክተናል ።

ስለዚህ አቅመ አዳም የደረሰ ነጋሢ ወጣት ሁሉ ምናልባት ፲፪ ወይም ፲፭ ዓመት ሲሞላው ወደዚህ ተራራ እየወጣ ይቀመጣል ። ስለዚህ ይህ ተራራ አንዳንድ ጊዜ ግሼን አምባ ተብሎ ባገሩ በግሼን ስም ሲጠራ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እላዩ ላይ በሚቀመጡት ነጋሢዎች ስም አምባ ነገሥት ይባላል (1) ። ላስተዳደርና ለጥበቃ አምባ ግሼንን የሚሾመው ለንጉሡና ለአገሩ የታመነ ትልቅ ሰው ነው ። በአሁኑ በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት የአምባ ግሼን ሹም የነበረው በሽምብራ ኩሬ ጦርነት በዠግንነት ሲዋጋ የሞተው ጸሐፌ ላም ሮቤል ነበር (2) ። ጸሐፌ ላም ሮቤል በዝሆን ዱር ጦርነት እንዳባቱ ወይም ካባቱ በበለጠ አስደናቂ ዠግንነት ሲዋጋ የሞተው የአዝማች ዓምደ ሚካኤል አባት ነው ። እርሱም በቤተ መንግሥቱ የታመነና የተከበረ ነበር ። በአምባ ግሼን ነጋሢዎቹን የሚጠብቅ በመሆኑ ከነዚያ ውስጥ አንዱን በሕዝብ ዘንድ የታወቀውን ይዞ ቢሸፍት አገር ለማነቃነቅ ስለሚ ችል ይኸን ከፍ ያለ እምነት ያለበትን ሹመት የሚሾመው የሚከበር ፤ የሚፈራ መሆን አለበት ።

ንጉሡ በበሽታ ወይም እርጅቶ በሞተ ጊዜ የቀኝና የግራ ቢትወደድነት ፤ የሊቀ ዓቢያን ብላቴን ጌታነት ፤ የጸሐፌ ላምነት ፤ የዓቃቤ ሰዓትነት ፤ የጽራግ ማሠ ሬነት ፤ የቄስ ሐጼነት . . . . . . ማዕርግ የያዙት የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች እገሌ ከአምባ ግሼን ወርዶ ይንገሥና ይግዛን ብለው መክረው በስ ምምነት ከጨረሱ በኋላ ያንድ ክፍል ጦር ይዞ አንዱ መኰንን ወይም የዚያው የአ ምባ ነገሥት ሹም ከጓደኞቹ ውስጥ የተመረጠውን ነጥለው የንጉሥ ልብስ አልብ ሰው ያወርዱትና እከተማው ሲደርስ ደንበኛ ሥርዓተ ንግሥ አድርሰው ያነግሡ ታል ። እርሱ በዚህ ዓይነት ሲነግሥ የእሥር ቤት ጓደኞቹና የሥጋ ወንድሞቹ እዚ ያው ቀርተው በዕድል የገጠማቸውን የግዞት ኑሮ ይቀጥላሉ ።

ቢሆንም የአምባ ግሼን ኑሮ ለነጋሢዎቹ ወጣቶች የከፋና ሥቃይ ያለበት እንደ እስር ቤት የሚቆጠር አይደለም ። በላዩ ላይ ሰፋፊ እርሻ ፤ ወንዝ ፤ ጫካ ያለ በት ስለሆነ በዘበኛ እየተጠበቁ በዚያው ባሉበት ተራራ እንደልባቸው ወዲያና ወዲህ ማለት መጫወት ይችላሉ ። እንዲያውም አምባ ግሼን ባዼ ናዖድ ዘመነ መን ግሥት ላይ እንደገለጽነው ለነጋሢዎቹ ልጆች የትምህርት ቤት ነው ማለት ይቻ ላል (3) ። ከፊደል ዠምሮ የቅኔ ፤ የዜማ ፤ የመጻሕፍት ትምህርት ስለሚሰጥ የትም ህርት ጣም ያለው ወጣት ሁሉ ለመንገሥ ሲወርድ ሊቅ ሆኖ ይወርዳል ። ዓፄ ናዖድ

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 97
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 103
(3) የኢት. ታሪክ ካዬ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 59 - 60 ፣

የተቀኙት ቅኔ ለእመቤታችን የደረሱት መልክ መዠመሪያ በዚህ በአምባ ግሼን (አምባ ነገሥት) ተምረው ነው (1) ። ያዔ ዘርዓ ያዕቆብ ሊቅነትና ደራሲነት ከዚሁ የግዞትና የትምህርት ቤት የመነጨ ነው ።

ደግሞ ከነጋሚዎቼ መካከል ወንድሞቼን ፤ ልጆቼን አሥሬ ከማን ጋር ልደሰት ነው በማለት "ልጅህ እንደ ወንድምህ በረታ አምባ ግሼን ሄዶ ይታሠር" እያሉ የሚያማክሩትን እያለፈ ለዘመዶቹና ለልጆቹ እየራራ ባጠገቡ አስቀምጦ ሹመትና ደረጃ እየሰጠ የሚያኖር ይገኛል ። የአቤቶሁን ፋሲለደስ ልጅ አቤቶሁን ሱስንዮስ ባዔ ሠርፀ ድንግል ቤተ መንግሥት በነበረበት ሰዓት መካሮች ወደ ንጉሡ ገብተው "ይህ ያቤቶሁን ፋሲለደስ ልጅ (ሱስንዮስ) እነሆ አደገ በረታ ስለዚህ ባገር ላይ ሁከት እንዳይነሣ እሥሮ ወደ አምባ ግሼን መላክ ይሻላል" ብለው ቢመክሩዋቸው ንጉሡ "እንደዚህ ያለው አስጠሊ ምክር ከአንደበታችሁ ዳግመኛ አይውጣ" ብለው እንደመለሱላቸው በዓዔ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ይገኛል (2) ። እንደዚሁም በሸዋ «ወንድሞችዎ አቤቶ ሰይፉና አቤቶ ዳርጌ አያስገዙዎትምና ይታሠሩ» ብለው አማካሪዎች አሳብ ቢያቀርቡላቸው ንጉሥ ኃይለ መለኮት «አላደርገውም ወንድሞቼን እሥሬ ከማን ጋር ልኖር ነው ፤ ማናቸውም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንምና ከፈቀደላቸው ይግዙ» ብለው መለሱ ይባላል (3) ።

በዚህ መካከል ልንመለከት የሚገባው እንደማናቸውም ሰው ሁሉ የነገሥታት ጠባይ አንድ አለመሆኑን ፤ አንዱ በክፋት ሲጠቀም ሌላው በደግነቱ መጐዳቱን ነው ። አንዱ ንጉሥ እንደ ዓፄ ሠርፀ ድንግል ISIC ያሰው በራሱ የሚተማመን በጥር ጣሬ ባሕር ውስጥ እየዋኘ ሰውን ለማጥፋት ማሠር መግደል የማይወድ ሌላው ደግሞ ነገ ሊደርስ የሚችለውን ዛሬ በማውጠንጠን ተቀናቃኙን ሲያንስ ካላሠረ ሲበዛ በማስገደል ካላጠፋ ልቡ ዕረፍት የማያገኝ አለ ። ያንዱ አስጠሊ የሌላው ተወዳጅ ቢሆንም ሁሉም የሚመራው በፍጥረቱ እንዳገኘው ዝንባሌ ነው ።

በታሪክ ውስጥ ለገዥዎች ርኅራኄያቸው ሲያስጠቃቸው ጭካኔያቸው ደግሞ የገዥነት ሥልጣናቸውን ሲያጸናላቸው ብዙ ጊዜ ይታያል ። አሁን በዚህ እላይ በተ ጠቀሰው የርኅራኄና የደግነት መንፈስ ዓፄ ሠርጸ ድንግል ለአቤቶሁን ፋሲለደስ ልጅ ለሱስንዮስ ራርተው ከእሥራት አድነው በነፃነት በተዉበት ምክንያት ንጉሡ ከሞቱና ልጃቸው ያዕቆብ በነገሡበት ሰዓት ሱስንዮስ ያዔ ያዕቆብ የዙፋን በይፋ ተፋላሚ ሆነው በመጨረሻም በጦርነት ከገደሉዋቸው በኋላ ለመንገሥ ቻሉ ። ሱስንዮስም በዚህ ዓይነት ያዕቆብን ገድለው ከነገሡ በኋላ የጐንደርን መንግሥት ለልጃ

(1) ካኙ ደብተሮ እምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. ፰
(2) "ዝንቱ ወልዱ ለአቤቶ ሁን ፋሲለደስ ናሁ ልህቀ ወኮነ ጽኑዓ ይሄይስ ይእስርዎ ወያንብርዎ ኀበ አምባ ዘግሸን በከመ ሥርዓቶሙ ለደቂቀ ነገሥት ፤ ከመ ኢይኩን ሀከክ ውስተ ብሔር ወመንሱት ውስተ ሀገር ። ወሰሚአ ንጉሥ ዘንተ ምክረ እኩየ ተቆጥዓ . . . . . ወሜጠ ሎሙ ቃለ ሰጣዌ እንዘ ይብል ዘከመዝ ነገር ኢይፃእ እምአፉክሙ ወኢትድግሙ እም ይእዜ . . . . . . የዓፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ፔሬይራ ያሳተመው ምዕ. ፩ ገጽ ፮ - ፰
(3) ሳይጠረዝና ሳይታተም የቀረው የብ. ጌ. ኅሩይ ጽሑፍ . . . . . . ገጽ 60

ቻው ለፋሲልና ለተወላጆቻቸው መሥርተው አለፉ ። በየጊዜው ያፄ ያዕቆብ ተወላ ጆች ቢነሡም "ወሬኛ" እየተባሉ ከመታሠርና ከመገደል እጅና እግር ከመቆረጥ በቀር ከዓፄ ልብነ ድንግል በልጃቸው ባፄ ሚናስና በልጅ ልጃቸው ባፄ ሠርፀ ድን ግል በኩል በቀጥታ ከነጋሢ አባታቸው የወረሱትን መንግሥት ሊያረጋግጥላቸው አልቻለም ። ስለዚህ የጐንደር የነጋሢነት ሥርወ መንግሥት ከያዕቆብ ቤት ወጥቶ ወደ ሱስንዮስ ቤት ተዛውሮ ኖረ ።

የጐንደር መንግሥት ካፄ ሱስንዮስ እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ ድረስ (፲፭፻፺፱ - ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ) በቆየበት ዘመን ሁሉ በየጊዜው ያፄ ያዕቆብ ተወላጆች በቀጥታ ባፄ ሠርፀ ድንግል የወረደው የነጋሢነት ዘርፍ በሱስንዮስ አነሣሥ በጋሎቹ ደጋፊ ነት የተነሣ ለነሱስንዮስ ከዚያም ለነፋሲል ፤ ለነዮሐንስ ፤ ለነኢያሱ በመተላለፉ እየቆጫቸው በየጊዜው ዙፋን ፍለጋ እየተነሡ እላይ እንዳልነው ሲታሠሩ ፤ ሲፈቱ እንደ አምባ ግሼን ጐንደር አጠገብ የሚገኘው ወህኒ አምባ ለነርሱ የግዞት አጽመ ርስታቸው ሆኖ ይኖር ነበር (1) ።

መካሪዎቹ እንዳቀረቡት ዓፄ ሠርጸ ድንግል አቤቶ ሱስንዮስን ለማስገደል እን ኳን ርኅሩኅ ልባቸው ቢያግዳቸው ለልጃቸው ባላንባ ነፃነት በመስጠት ፈንታ በአ ምባ ግሼን ማጋዙን ቢቀበሉ ኑሮ ልጃቸውና ተወላጆቻቸው ዙፋናቸውን ለመነ ጠቅ ባልቻሉ ። እዚህ ላይ ለመግዛት መግደልና ማናቸውንም ወንጀላዊ ተግባርም ቢሆን መፈጸም እንጂ ርኅራኄ አይገባም የሚለው የኒኮላ ማኪያቬሊ ፍልስፍና ሥፍራ አለው ። የዓለም ገዥነት ሕይወቱ በጭካኔና በክፋት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያገራችን ሊቃውንት "ዓለምሰ ትቀውም በእኪት ፡ ዓለም ቆሞ የሚሄደው በተ ንኮል ነው" ያሉት ሐቀኛ አስተያየት መሆኑን እንገነዘባለን ።

አሁን የዚህን ጉዳይ ትተን በዚህ ዓመት የግራኝ የጦር አለቆች የዚህኑ የአምባ ግሼንን ተራራ ለመያዝ ፈትነው ሳይሳካላቸው ቀርቶ እንዲያውም ለመዠመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖቹ በውጊያ ቀንቷቸው ታላላቆቹን የግራኝን የጦር አለቆች አንዱን በመማረክ ሊላውን ሲገድሉ በሚቀጥለው ምዕራፍ እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፳፮

### ገራድ አህሙሹ ንጉሡን ፍለጋ ሄዶ አጥቶ ሲመለስ አምባ ግሼንን እንደወጋ በአምባ ግሼን ጦርነት የግራኝ ጦር መሸነፍ — የአህሙሹ መማረክ ፤ የገራድ ማታ ንና የአውራይ ኡስማን ሞት (፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ኅዳር)

ከግራኝ አህመድ በፊት ዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን በነገሠ በ፲፬ኛው ዓመት በ፲፫፻፳፭ ዓ. ም. የኡመር ወላስማ አራተኛው ትውልድ ሳብር አዲን መሐመድ (2) እንዳሁኑ

(1) የዮሐንስ የኢያሱ የበካፋ ዜና መዋዕል ጉይዲ ያሳተመው (Corpusco) ገጽ 288-289 ያፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድና ያፄ ኢዮአስ ዜና መዋዕል ገጽ 55 - 74

(2) ግዕዙ ሰብረዲን የሚለው

እንደ ግራኝ አህመድ ተነሥቶ በመላዋ ኢትዮጵያ ላይ እነግሣለሁ ፤ አብያተ ክርስ ቲያናቱን አፍርሼ ሕዝቡን በኔ ሕግ አስተዳድራቸዋለሁ ብሎ በኩራት መነሣቱን ለመግለጽ ግዕዛዊው ታሪክ እንደዚህ ይላል ። "አዕበየ ርእሶ ንጉሠ ዕልዋን ዘስሙ ሰብረዲን ወተመክሐ ላዕለ እግዚኡ ዓምደ ጽዮን ወይቤ እከውን ንጉሠ ላዕለ ኩሉ ምድረ ኢትዮጵያ ወእምለኮሙ (ወአመልኮሙ) ለክርስቲያን በከመ ሕግየ ወእመዘብር አብያተ ክርስቲያን . . . . . ." (1) ።

ሰብረዲን በዚህ ምኞት የአዳልን ፤ የሱማሌን ሕዝብ ሰብስቦ ከተነሣ በኋላ እንደ ግራኝ አህመድ ወጣትነት ፤ ዠግንነት የተዋሐደው ዓፄ ዓምደ ጽዮን ተዋግቶ መለሰው (2) ። ከ፪ መቶ ዓመት በኋላ እነሆ ግራኝ አህመድ ለሰብረዲን ያልሆነለ ትን ተነሥቶ ሲፈጽም እንመለከታለን ። ሊፈጽም የቻለውም ለግራኝ አህመድ የራሱ ዠግንነትና ዘዴኛ መሪነቱ በጠላቱ ግንባር ካለው ካልተሟላ ድርጅት ጋር በመጋጠሙ መሆኑን ያለፉት ሁሉ ምዕራፎች ያለ አድልዎ አመልክተውናል ። ስለዚህ ግራኝ ባለፈው ሁሉ እንዳየነው አብያተ ክርስቲያናቱን ከማቃጠል ሕዝ ቡን ከማስለም ጋር በአሳቡ ያለው ዋናው የአሁኑ ሰዓት ምኞቱ ንጉሡን ለመማረክ ነው ። እንደማናቸውም ወራሪ የንጉሡ መማረክና በእጁ መግባት ወይም በጦርነት መሞታቸው በመላው ኢትዮጵያ ገገርነቴን ያረጋግጥልኛል ብሎ ያምናል ።

ዓፄ ልብነ ድንግልን ግራኝን በጊዜያቸው አሥነስቶ እግዚአብሔር የጐዳ ቸው ቢሆንም ሁል ጊዜ ከእጁ ለጥቂት ስለሚያመልጡት በባላጋራቸው እጅ እን ዲወድቁና እንዲዋረዱ ስለ አላደረጋቸው ባለውለታው ናቸው ። ከሺምብራ ኩሬው ጦርነት ወዲህ እርሱ እንዳባረረ እርሳቸውም እንደሸሹ እርሱ ጋብቻ እንደጠየቀ እርሳቸው ኮርተው እምቢ እንዳሉ ድንገት አዘንግቶ ሊይዛቸው ሲል ለጥቂት እንዳ መለጡ በመጨረሻ ሲያክሙ እግዚአብሔር በትግሬ ግዛታቸው በፈጠረላቸው ከላይ ገመድ ካልተላከ በቀር ማንም ሰው ሊወጣበት ወደ ማይችለው ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ ወጥተው ከአገር አገር በስደት ከመዞር የመሸነፍን መራራ ወሬ በየቀኑ ከመስማት የልጆቻቸውን ፤ የወገናቸውን ሥቃይ ከማየት በእግዚአብሔር እጅ አረፉ ። ይኸንንም የምናነበው ወደ መጨረሻ ነው ።

ያረፉት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ሲሆን አሁን ያለነው በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. ላይ ስለሆነ የመከራው ጽዋ ገና እንደሞላ ነው ። ስለዚህ ኃይለኛው ግራኝ በዋስል አሸንፎ ካባ ረራቸውና እነዚያን ስመ ጥር አብያተ ክርስቲያናት በዝብዞ ካቃጠለ በኋላ እርሳቸ ውን ከመከታተል አላረፈም ። የሄዱበትን ለመሰለል እንደነ አናንያ ፤ እንደነ ሐይቢ ያሉ የወገን ጠላት ሞልተዋል ። ከነዚህም በቀር በአሁኑ ሰዓት ያሉበትን ብመራ ምን ታደርጉልኛላችሁ የሚል ከባላገርም "መጥፎ ባላገር" በጠባይ ከነአናንያ የሚዛመድ አልጠፋም ።

ስለዚህ አሁን በዚህ ምዕራፍ እርሳቸውን ለመከታተል ገራድ አህሙሽ የበ

(1) guerre d'Amde Syon page 279-280……

(2) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ም. 10 - 16

ላይ መሪ ሆኖ በርሱ ውስጥ የቀድሞ ሹማቻቸውና በኋላ የከዳቸው የይፋቱ ገዥ አውራይ ኡስማን የሱማሌው ባላባትና የግራኝ አማች ገራድ ማታን ብዙ ጦር ይዘው ሄደው ንጉሡን ተከታትለው ማግኘት አቅቷቸው ሲመለሱ አሸናፊነትና ዘረፋ ያሰከረው ዋናው መሪ ገራድ አህሙሽ ተራራውም የማይደፈር ነው መሪያችንም ይማም አህመድ አምባ ግሸንን ውጉ ብሎ አላዘዘንም ይቅርብን እያሉ የመከሩትን የነሸሪፋ ኑርን ምክር እምቢ ብሎ አምባ ግሼንን ወጋ ። በዚያም እላይ ካሉትና ለእርዳታ ከመጡት ከነቢትወደድ ሠርፄ ጋር ሲዋጋ እንደምን እንደተማረከ ገራድ ማታንና አውራይ ኡስማንም በምን አኳኋን እንደሞቱ ከዚያው ከምንጩ ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ ከዚህ እንደሚከተለው እናንብብ ።

«በዓባዊ (ዓባይ) ና በአምሐራ መካከል በዋላህ ወዳሉት የጥንት ነገሥታት ወደ ሠሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ፤ ክርስቲያኖቹ ተሰብስበው ተደብቀዋል የሚሉ ወሬ ስለሰማ ይማም ዘሐርቡይ መሐመድን አቡበከር ቀጢንን . . . . . ጨምሮ አውራይ አቡንን የበላይ አድርጎ ነጭ ባንዲራ አሲዞ ወደዚሁ አገር ላከው ። የጦሩ ልክ ፪፻ ፈረሰኛ ፭ሺ፭፻ እግረኛ ነው ። የያዙት መሪም አዝማች ሐይቢ ነው ። ተጉዘውም ዋላህ በደረሱ ጊዜ አራት አብያተ ክርስቲያናት አገኙ (1) ። ከነዚሁ ሁለቱ በወርቅ የተጌጡ ሁለቱ ግን አምረው የተሠሩ እንጂ የወርቅ ሥራ የለባቸውም እስላሞቹ ወደ ውስጥ ገብተው ወርቁን በመጥረቢያ እየመቱ ከየግድግዳው ላይ ማንሣት ዠመሩ ። ሁሉንም አንሥተው ከጨረሱ በኋላ በእንጨት ወደ ተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ገብተው ብዙ የወርቅ ጥጃ የሚመስል (ጽላት) በአራት እግር ባለው ላይ (መንበር) የተቀመጡ አገኙ ፤ የነርሱም ሚዛን ያንዱ ፩ሺ ወቄት የሌላው ፩ሺ፭፻ ወቄት ይሆናል ። ሹማምንቱ እንዳጋጠማቸው ይኸን ሁሉ አንሥተው የሐር ልብሱን ሁሉ አውጥተው ሲጨርሱ አራቱንም አቃጠልዋቸው ።

አውራይ አቡን ወደዚህ አገር በተላከ በ፪ኛው ቀን አንድ ክርስቲያን ወደ ወዚር ኑር መጣና "ንጉሡ ፲፭ ፈረሰኞች ብቻ ይዞ ተደብቆ የተቀመጠበትን ሥፍራ አውቃለሁ ባሳያችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ" ብሎ ጠየቀው ወዚሩም የፈቀድኸውን ያህል ገንዘብ እንሰጥሃለን ከግብርም ነፃ ትሆናለህ ቢለው እሺ እንግዲያው ተከተሉኝ ልምራችሁ አለ ። ከዚህ በኋላ ወዚር ኑር ለገራድ አህሙሽ ነገረውና ሁለቱም ተያይዘው ወደ ይማም ገብተው ይኸንኑ ነገሩት ። ቀጥሎም ወዚሩ እኔ ወይስ አህሙሽ ይሂድ ብሎ ቢጠይቀው ይማም ገራድ አህሙሽ ይሂድ ብሎ መለሰ ።

ከዚህ በኋላ አህሙሽ የበላይ አዝማች ሆኖ በውስጡ አውራይ ኡስማንን ፣ ፋራቃሃም ሳጡንን ፣ ሻምሱን የባሕር ወታደሮች አለቃን ፤ አባስን የይማምን የወንድም ልጅ ጨምሮ መሪውን እፊት እፊቱ አድርጎ ሄደና ንጉሡ አለ ወደ ተባለበት ቦታ ደረሱ ። ነገር ግን ንጉሡን አላገኙም ። መሪውን ወዴት አለ ንጉሡ ብለው ቢጠይቁት እዚህ ነበር ይኸውና የነደደው እሳት ያስታውቃል ብሎ መለሰ በዚያን ጊዜ አህሙሽ ፈረሰኞቹን ወደ ባላገር ላከ ። እነሱም ሁለት የባላገር ሰዎች ይዘው

(1) በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ዋላህ የሚለው የዋድላን አገር መሆኑ ነው ።

ISIC

ቢጠይቋቸው ንጉሡ እዚህ ነበረ ነገር ግን እናንተ ያላችሁበትን ሠፈር እሳቱን ሌሊት ቢያይ ከዚህ ተነሥቶ የባሽሎን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ቤገምድር ግዛት ሄደ ብለው ነገሩዋቸው ። ከዚህ በኋላ አህሙሹ ጦሩን እንዳስከተለ ፪ ቀን ሙሉ ንጉሡን ሲከታተል እስከ ባሽሎ ወንዝ ደረሰ ። በዚያ ሆነው ንጉሡን ልናገኘው አንችል ምና ወደ ይማም ብንመለስ ይሻላል ተባብለው ሁለት ቀን ተጉዘው ባንድ ሥፍራ ላይ በደረሱ ጊዜ ገራድ አህሙሹ ወታደሩን ሁሉ ሰበሰበና አምባው (አምባ ግሼን) ይኸውና ስለዚህ ወደርሱ ሄደን ከበን እንያዘው ብሎ ተናገረ ፣ በዚያን ጊዜ ሼሪፍ ኑር ከጓደኞቹ ጋር ተስማምቶ ብድግ አለና አምባው በጣም አስቸጋሪ ነው ። ተራራው በጣም ከፍ ያለ . . . . . . ዙሪያውም ተመሽጎ የሚጠበቅ ነው ። በመሰላል ካል ሆነ በቀር ወደዚያ ማንም አይወጣም ይማምም አምባውን ውጉ ብሎ አላዘዘምና ዝም ብለን ወደርሱ ብንመለስ ይሻላል ብሎ ቢናገር የጦሩ አለቃ እኔ ነኝ ወይስ አንተ ብሎ ጠየቀው ። ሸሪፉም አንተ ነህ ብሎ መለሰለት ፣ አህሙሹም እንግዲያው አለቃው እኔ ከሆንሁ እዚህ ንግግር የለም ዝም ብላችሁ ታዘዙኝ አለና ጉዞው ተዠመረ ። ሽቅበትና ቁልቁለት ወንዛወንዝ የሞላበትን አስቸጋሪውን መንገድ አል ፈው ወደዚሁ ወደ ተባለው አምባ ደረሱ ፣ በደረሱም ጊዜ ትልቅ ገደል መሆኑን ያለ መሰላልም የማይወጣ መሆኑን ተገነዘቡ ። እተራራው (አምባው) ላይ የነገሥታቱ ልጆች የሚቀመጡበት ከሺ የሚበልጡ ቤቶች አሉ ። ወንዝም እርሻም አለበት ።

አንድ ንጉሥ ወንዶች ልጆች በኖሩት ጊዜ በመንግሥቱ ላይ ሁከት እንዳይፈጥ ሩበት ወደዚሁ ተራራ ልኮ ያስቀምጣቸዋል ። ንጉሡ በሞተ ጊዜ ከነዚህ አንዱን ከአ ምባ አውርደው ያነግሡታል ። ይህ ከአባት ከአያት ከቅድም አያት የወረደ ልማዳ ቸው ነው ። አምባው ላይ ፪ሺ፫፻ የሚሆኑ ልዑላንና ልዑላት ነበሩበት ። ለነዚህም ንጉሡ ምግባቸውንና ልብሳቸውን በየጊዜው ይሰጥ ነበር ። አህሙሹ አምባው ጥግ በደረሰ ጊዜ እበሩ ላይ ሌሊቱን ሁሉ ተዋጉ ። እስላሞቹ መሰላል ይዘው ለመውጣት ዙሪያውን ይዞሩ ዠመር ። ነገር ግን ክርስቲያኖቹ መብራት በእጃቸው ይዘው ዙሪያ ውን አፋፍ ላፋፍ እየዞሩ ሙተላለፊያውን ይቆጣጠሩ ነበር ። እስላሞቹ ከታች መሰ ላላቸውን እገደሉ ላይ ለጥፈው ለመውጣት ሲሞክሩ እነዚያ ከላይ የናዳ ድንጊያ እየ ለቀቁ ወደኋላ ሲመልሱዋቸው ብዙ ጊዜ አለፈ ።

ከዚህ በኋላ አብደላ ቤን ናስር ፣ ናስር ቤን ዳላን ፣ ሸሪፍ ኑር ፣ አዲቅ ተክለ ኢየ ሱስን የገደለው ፣ ሰይድ ፣ አናስ ፣ አብደላ ሱማሌው ፣ እነዚህ ሰባት ጕበዛዝት ተመ ርጠው በዚች ሌሊት እዚህ አምባ ላይ ሳንወጣ አናድርም ብለው ተማማሉ ። ከዚያ በድብቅ በእጃቸውና በእግራቸው እየዳሁ መውጣት ዠመሩ ። ከላይኛው ተራራ በታች እበሩ ላይ ሆኖ የሚጠብቀውን ዘበኛ ተቀምጦ ሲጠብቅ አዩት የሚያስ ወጣው ሦስቱም በር በዘበኛ ይጠበቃል ። ዘበኞቹ እበራፋቸው ሆነው እሳት እያነ ደዱ ሲጠብቁ ያንደኛው በር ጠባቂ ተቀምጦ አዩትና ወደዚህ ወደ ተቀመጠው እን ሂድና እሳቱ ሲጠፋ እንቅልፍ እንደወሰደው እናውቃለን እሳቱ እስኪጠፋ እዚሁ አለንበት ሆነን ዝም ብለን እንጠብቅ ተባባሉ ፣ እንቅልፍ ወስዶት እሳቱ እስኪ ጠፋ ታግሠው እንደቆዩ እሳቱ ጠፋ በዚያን ጊዜ ናስር ቤን ዳላን ጓደኞቹን ከኋላ

ISIC

አስከትሎ በእጃቸውና በግራቸው እየዳሁ ወጥተው እበሩ ላይ ደረሱ ። እሬት ያለው ናስር ዘበኛውን ለማረድ ጩቤውን ከወገቡ አውጥቶ በእጁ ያዘው ደክሞት ነበርና ፪ ሦስት ጊዜ እየተንገደገደ እንደተራመደ ክርስቲያኑ ነቃና ከጓደኞቹ ጋራ "ሌባ ሌባ" እያሉ ጮኹ በናዳና በድንጋይም እየወረወሩ መለሱዋቸው እስላሞቹም ደንግጠው አንዱ ባንዱ ላይ እንደተደራረቡ ቁልቁል ሸሹ ። ሸረፍ ኑር ግን ጓደኞቹ ቁልቁል እየተንከባለሉ መውረዳቸውንና ሊደርስባቸውም እንደማይችል ተገንዝቦ እዚያው አጠገቡ አንድ ቋጥኝ ሥር ተቀምጦ ሲነጋ ቀስ ብሎ ወርዶ ከጓደኞቹ ተደባለቀና እንኳን እግዚአብሔር አወጣን ተባባሉ ።

አውራይ ኡስማን ጦሩን ይዞ ባንደኛው በር አህሙሹ በሁለተኛው በር ሆነው ይዋጉ ነበር ። አውራይ ኡስማን ሌሊቱን ሁሉ ከክርስቲያኖቹ ጋር የጠበቀና የከፋ ጦርነት ሲያደርግ አደረ ። ቢሆንም ክርስቲያኖቹ ወደ ኋላ ሸሹ ። ከእስላሞቹም ምርጥ ጉበዝ የሆኑት እነፈንጅ ሰበር ፣ እነባል ሱር ኢብራሂም ክርስቲያኖቹን እየተከታተሉ ካንደኛው በር እስከ ሁለተኛው በር አድርሰዋቸው ነበር ፤ ፪ኛው በር በብረት ዘንግ ተጠምጥሞ ተዘግቶ ነበር ። እስላሞቹም እርሱን ለማፍረስ ሲያበድቡ ክርስቲያኖቹ ማሰሮ የሚያካክል ድንጋይ ከበላያቸው ሆነው እየወረወሩ መልሰው ወደታች አወረዱዋቸው ።

ከዚህ በኋላ ገራድ አህሙሹ እምባውን ከብቤያለሁና ድረስልኝ ብሎ መልክተኛ ወደ ይማም ላከ ። ይማም ደብዳቤውን ከመልክተኛው ተቀብሎ አነበበና ወደዚያ ሂዱ ብሎ ማን አዘዛችሁ ብሎ ቢጠይቀው ንጉሡን ፍለጋ ሄደን አጥተን ስንመለስ ገራድ አህሙሹ አምባውን እይዛለሁ ቢል እስላሞቹ አሳቡን አልተቀበሉም ነበር ። ነገር ግን አለቃችሁ ነኝና ታዘዙ ብሎን ወደዚያው ሄደን ሌሊቱን ተዋጋን ብሎ መለሰለት ። ሥፍራው ለፈረሰኛ ይመቻል አይመችም ብሎ ቢጠይቀውም ለፈረሰኛም ለእግረኛም አይመችም የሚወጣው በመሰላል ነው ብሎ መለሰለት ። በዚያን ጊዜ ይማም ቅደምና ቆየኝ እኔም እከተልሃለሁ ለነአህሙሹም አሁን ያላችሁበትን ሥፍራ ትታችሁ እኔ እስከመጣ ድረስ ሰፋ ያለ ቦታ ላይ ሠፍራችሁ ቆዩኝ ብለህ ንገረው ብሎ መላከተኛውን መልሶ ላከውና ሄደ ፤ መልክቱንም ለአህሙሹ አደረሰ . . . . . ይማም ወደ አምባው ፫ ቀን ተጉዞ ያንድ ቀን መንገድ ሲቀረው ሰፈረ ።

ከዚሁ ጊዜ ቀደም ብለው በአምባው ላይ ያሉት የክርስቲያን መሣፍንት በእስላሞቹ በጥብቅ መከበባቸውን ባዩ ጊዜ ጠላት በጥብቅ ከተማችንን ከቧል ተሸንፈን ሳንሰጥ ጦር በቶሎ ይድረስልን ጦሩ የቆየ እንደሆነ በግድ ሳንወድ ተሸንፈን ማስረከባችን አይቀርም ብለው ወደ ንጉሡ ልከው ነበር ። ንጉሡም የነሱን መልእክት ከሰማ በኋላ ቢትወደድ ሠርጼን ፤ የራስ ዓምዱን ልጅ ፤ አዝማች ዮናኤልን ፤ አዝማች ይስሐቅን ላካቸውና አውራይ ኡስማን አምባውን በሰበረበት በዚያው ሌሊት በአንጎት በኩል ደርሰው ጧቱን ወደ እስላሞቹ ተጠጉና ጦርነት ገጠሙዋቸው ። እስላሞቹም የክርስቲያኖቹን መምጣት አልጠረጠሩም ነበርና ዝም ብለው ወደፊታቸው ያለውን አምባውን ብቻ ይወጉ ነበር ፤ ክርስቲያኖቹም የደረ

ሱት አውራይ ኡስማን በሩን ይዞ እምባውን በሚወጋበት በኩል ነበር ። አውራይ ኡስማን ፈረሶቹን አህሙሹ ዘንድ ትቶ በእግሩ ነበር ፤ ስለዚህ ክርስቲያኖቹ እንደ ተጠጉት ሲያውቅ ጦሩን በንግግር አነቃቅቶ ሰይፉን ይዞ ጋሻውን ደግኖ . . . . . ሥፍራው ለፈረስ ጦርነት የማይመች ስለነበረ ክርስቲያኖቹም ከፈረሶቻቸው ወር ደው ጋሻና ጦራቸውን ይዘው ጦርነት ተጋጥመው ኃይለኛ ውጊያ አደረጉ ። ከክርስ ቲያኖቹ ውስጥ የአጋሜና ሲምት የሚባሉ የትግሬ የቀስተኛ ጦር አብሮ ነበር ከእስ ላሞችም ውስጥ ፈረሰኛው አሊ ኤል ዋራዲ ፤ ፈንጂ ሳብር . . . . . . ሰንበታይ ከባ ሕር (ከዓረብ) የመጣው ኃይለኛ ተዋጊ ነበሩ ፤ እነዚህ ሁሉ አውራይ ኡስማን ፊት አስደናቂና አደገኛ ውጊያ እያደረጉ አራት ጊዜም ክርስቲያኖቹን እያሸነፉ . . . . . መለሱዋቸው ። ክርስቲያኖቹም ፫ ጊዜ እያፈገፈጉ በ፬ኛው ጊዜ ተመልሰው መጥ ተው እንደገና ጽኑ ውጊያ አደረጉ ፤ ወታደር ለወታደርም ተደባልቆ ይማታ ዠመር "አሊ ኤል ዋራዲም እክርስቲያኖቹ መካከል ገብቶ ሲዋጋ ደረቱን አንድ ትግሬ በጦር መትቶት ወደቀ ፤ እንደወደቀም "በካዓባህ በጌታው እኔ መንግሥተ ሰማያ ትን አግኝቻለሁና እኔ ምንም አልሆንም ይልቅስ ሳትፈሩ ጠላትን ውጉ" ብሎ ተና ገረ ኤሚር ጃፋት አሊን መትቶ የጣለውን ሰውዬ ተመልክቶ በላዩ ላይ ወደቀበትና መትቶ ገደለው ።

ክርስቲያኖቹ እያደር ስለበረከቱና በመርዘኛ ቀስታቸው ክፉኛ ስለተዋጉ ከፈ ንጅ ሰበር በቀር እስላሞቹ ሸሹ ። ፈንጅ ሰበር ግ[illegible]ደ አበደ ግመል ሆኖ ጓደኞቹ ሲሸሹ እርሱ ብቻውን ሰይፉንና ጋሻውን እንደያዘ እየተዋጋ አንዱን ክርስቲያን በሰይፉ ፊቱን መትቶ ጣለው ። ጋሻውም መጨበጫው ብቻ እጁ ላይ ሲቀር የቀ ረው በሰይፍና በጦር ተደብድቦ ወደቀ ። እንደዚህ አድርጎ ከተዋጋ በኋላ ወደሚሸ ሹት ጓደኞቹ ሄዶ ተደባለቀ ። በዚህ ጦርነት ግንባር አውራይ ኡስማን . . . . ሞተ ፤ አሊ ዋራዲ እወደቀበት ላይ ሞተ ። የቀሩትም ከተራራው መካከል ሸሽተው ወር ደው እሜካ ገብተው ተቀመጡ ።

ገራድ አህሙሽና ወታደሩ የአውራይ ኡስማን ጦር ተሸንፎ ከተራራው እየ ሸሸ ሲወርድ አይተው ወደነዚያ ሄደው ዶጇን ከነበረው ጦር ጋር ሆነው የሸሸው ንም አበረታትተው ውጊያውን እስከ መጨረሻ ትንፋሻቸው ድረስ ቀጠሉ ። በዚህ ጦርነት አስደናቂ ጉብዝናቸውን ያሳዩ የባሕር ወታደሮች አሊቃ ፤ ሻምሱ ፤ ሱተ ላይ ወሰን ግን ናቸው ። ቢሆንም ጦሩ ተሸንፎ ሸሸ ፤ ገራድ አህሙሽም ተማረከ ፤ ሱማሌው ገራድ ማታን ፤ አብደላ ቢን ናስር . . . . . . ሳሊህ ፤ ኡመር ፤ ሰይድ ፤ ሱማ ሌው አሊ ዱቃላይ ሞቱ ። ክርስቲያኖቹ ፲፭ ፈረሶች ማረኩ ይኸም የሆነው በ፲፬ ረቢ ፱፻፴፰ የሂጅራ ዓመት ረቡዕ ቀን ነው (1) ።

አሸናፊዎቹ ክርስቲያኖች የሞቱትን የእስላሞች ጭንቅላት ቆርጠው ከተማረ ኩት ፈረሶች ጋር ለንጉሡ አቀረቡዋቸው ። መሣፍንቱና ክርስቲያኖቹ በዚህ ቀን ታላቅ ደስታ አደረጉ ። ገራድ አህሙሽም እንደታሰረ ቀርቦ ጥቂት ቀን በወህኒ እንደ

(1) በኅዳር ወር በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም.

ሰነበተ ተገደለ ፡፡ ከርሱ ጋር የዘመተው ጦር በሽሽት ወደ ይማም ደረሰ ፡፡ እርሱም ወደ አምባው ይጓዝ ነበረና የሆነውን ሁሉ ነገር ሸሽተው ከመጡት እስላሞች እንደበት በሰማ ጊዜ ታላቅ ኀዘን አደረገ ስለአማቹ ስለማታንም አለቀሰ ፡፡

ከዚህ በኋላ በዚህ ጦርነት የነበረው ሹምና ወታደር ሁሉ ይሰብሰብ ብሎ እዘ ዘና በተሰበሰቡ ጊዜ ተቀመጡ ብሎ “አውራይ ኡስማንና ጓደኞቹ ብቻ ተዋግተው አውራይና አሊ ዋራዲ መሞታቸውን ሰማን ፤ እናንተ ግን ከገራድ አህሙሽ ጋር የነ በራችሁት መዋጊያ መሣሪያና ፈረስ እያላችሁ አለቃችሁን አጋልጣችሁ ሳትዋጉ ሸሽታችሁ መጥታችሁ” አላቸው ፡፡ እነሱም መሬት መሬት ብቻ እያዩ ምንም ሳይ መልሱ ቀሩ ከዚህ በኋላ ዋና ዋኖቹን ፋራቃሃም አሊን . . . . . . ገራድ አህማዱሽን፡ መቶ የሚሆኑትን ፈረሰኞች አሲዞ አሣሠራቸው ፡፡ ሊገድላቸውም ቆርጦ ነበር ፡፡ ነገር ግን ሸኮቹ (ቀሳውስቱ)ና ኤሚሮቹ (መኳንንቱ) በመካከል ገብተው አማል ደው አስፈቷቸው ፡፡ ሲፈቱም ይማም እንደዚህ አላቸው ፤ እንደዚሁ አልተዋችሁም ነገር ግን እናንተን ወደ አምባው ይገፎ ሄጀ ትዋጋላችሁ መኳንንቱም በዚህ ተራ ራና አስጨናቂ ሥፍራ ላይ ሁላችን እንድናልቅ ከፈቀድህ ውሰደን ያለዚያ እግዚአ ብሔር ድሉን እንኳን ቢሰጥህ ከመሳፍንቱ ልጆች በቀር በዚህ አምባ ላይ የምታገ ኘው ነገር የለም ፡፡ ወታደርም ፣ ፈረስም በዚያ አይገኝም ፤ ለሀብት እንደሆነ እግዚ አብሔር ይመስገን ይኸው እንዳፈር ሆኖ ሰው ሁሉ ሀብቱን መሸከም አቅቶት ይከ ሚል ፡፡ ሀበሻ በሙሉ ገና አልተያዘም ደዋሮ ፣ ባሌ ፣ ሻርካህ ፣ ሃድያ ፣ ዋጅ ፣ ዳሞት ገና ጨርሰው አልገበሩም ፡፡ በእነዚህ አገሮች በያንዳንዱ አውራጃ የእግረኛውም የፈ ረሰኛውም ክርስቲያን ወታደር ከነአለቃው እንዳለነው ስለዚህ ወደኋላችን ተመል ሰን ፈጠጋር ካለው ጦራችንንና ከወዚር አዶሌ ጋር እንደባለቅ ብለው መለሱ ለት ፤ ይማም ይኸን ንግግር አዳምጦ ከአሰላሰለ በኋላ እውነታችሁን ነው ብሎ መለሰ ፡፡ ከዚህ በኋላ አምባውን ትተን እነዚህን አገሮች እንውጋ ካላችሁ በል አንተ እናንያም እንደዚሁ ካልሀ ወደነዚሁ አገሮች ምራን አለው እርሱም እሺ ጌታዬ መንገዱንም አገሩንም ደህና አድርጌ አውቃለሁ አለ . . . . .» (1) ፡፡

ዓረብ ፋቂህ በዚህ ምዕራፍ የወገኖቹን የነገራድ አህሙሽን ሙተና ፍጻሜ በዚህ ዓይነት ዘርዝሮ ባመለከተበት ላይ ገራድ አህሙሽ ንጉሡን ተከታትሎ ለመ ማረክ ወይም ለመግደል እንጂ አምባ ግሼንን ለመውጋት አለመላኩን ገልጾልናል፡፡ ነገር ግን በዚህ ዘመን የእስላሞቹ አለቆች ሁሉ ጊዜ ሰጥቷቸው በየጊዜው በያለበት ድል በድል እየተከታተለ ስለአጋጠማቸው አባቶቻቸው ደርሰውበት በማያውቁት ታላላቅ የኢትዮጵያ አውራጃ ደርሰው ብዙ የወርቅ ፣ የብር ፣ የሐር ልብስ ሀብት ስለ አገኙ በዚህም ላይ ግራኝ ተዋጉ ብሎ ባያዝም ቅሉ ዘማች የጦር አለቃ ወዳንድ የጦር ግንባር ሲሄድ ይሁን ወይም ሲመለስ በፊቱ ያገኘውን ቤተ ክርስቲያን ቢያ ቃጥል ፤ ሀብት ቢዘርፍ ግራኝ እንደሚደሰት እንጂ እንደማይቆጣ ስለሚያውቅ በዚህ ሁሉ ምክንያት ገራድ አህሙሽ አምባ ግሼንን በቀላሉ ይዞ ሀብቱን ለመዝ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 316 - 326

ረፍ እንደሚችል ተማምኖ ነበር ። ባለፈው የተገኘው ድልና ሀብት ስላሰከረውና በክርስቲያኖቹም ላይ ንቀትን ስለአሳደረበት "አይቻልም" ብሎ የመከረውን ሸረፍ ኑርን አለቃው እኔ ነኝ ወይስ አንተ ብሎ ገሥጾ ሊዋጋ ሄደ ። ነገር ግን ጠላትን መናቅ በቀድሞው ጊዜ ለክርስቲያኖቹ እንዳልጠቀመ አሁንም አህሙሹ ወገኖቹን አስጨርሶ እርሱም በነቢትወደድ ሠርፄ እጅ ተማርኮ ወደ ንጉሡ ሄደ ። ታሥሮ በሚሄድበት ጊዜ የሸረፍ ኑር ምክሩና የርሱ እምቢታ ትዝ እያለው ሳይገርመው አይቀርም ። የተዋጋው በእልህ ስለሆነ ይኸን የመሰለ የእልህ ስሕተት ግራኝን አይገጥመውም ። አሁንም በእልህ የወገኖቼን ደም ልበቀል ብሎ ወደ ግሺን አምባ አልሄደም ።

የርሱ መማረክ የነገራድ ማታን ሞት ግራኝን እስከማስለቀስ ሲያደርሰው በዚያው መጠን እንደዚህ ያለ ድል አጋጥሟቸው የማያውቁት ድል አድራጊነት የናፈቃቸው ንጉሡና ወገኖቻቸው እንደሚደሰቱ የታወቀ ነው ። አህሙሽም ገራድ ማታንም ባለፉት በባደቄ ፤ በሽምብራ ኩሬ በዝሆን ዱር በዋስል ጦርነት እየተዋጉ በንጉሡ ጦር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ያደረጉ ስለሆኑ የነዚህ የስመ ጥር ጠላቶቻቸው መውደቅ ንጉሡን በዚያን ዕለት እንደሚያስደስታቸው ግልጽ ነው ። ይልቁንም አውራይ ኡስማንን አክብረው ፈጠጋርንና ይፋትን የሚያካክሉ ታላላቅ አውራጃዎች ሰጥተው በግዛት አስቀምጠውት ሳለ በታማኝነት ሊዋጋ ከንጉሡ የተቀበለውን ጦር ይዞ ከከሐዲው ምክትሉ ከአናንያ ጋር ለግራኝ ገብቶ ከዚህ ወዲህ ባሁኑ ጊዜ ምክር እየሰጠ ምስጢር እየገለጸ መንገድ እየመራ እየተከታተለ ይወጋቸው ስለነበረ የርሱን ሞት ሲሰሙ የበለጠ ደስታ ይሰማቸዋል ።

ከዚህ ጋር ልንመለከት የሚገባው የግራኝን የዲሞክራሲነት መንፈስና የአህሙሽን የዲክታተርነት ጠባይ ነው ። አህሙሽ ጓደኛው ሸረፍ ኑር ምክንያቱን አስረድቶ አምባውን መውጋት ይቅርብን ቢል በእልቅናው ተመክቶ አይሆንም ብሎ ጦሩን አስጨርሶ እርሱ ራሱ ተማርኮ እስከ መገደል ደረሰ ። ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው ግራኝ አህመድ ግን ሄደን አምባውን እንውጋ ብሎ በእልህና በንዴት ቢነሣ የጦር አለቆቹ ሄደን ብናልቅ ጥቅም የለውም ድል ብናደርግም በተራራው ላይ ከመሳፍንት ልጆች በቀር የምናተርፈው የለንምና ይልቅስ ጨርሶ ወደ አልተገዛው አገር እንሂድ ቢሉት ንዴቱን ውጦ ፤ እልሁን አቀዝቅዞ ማዘዝ ሲቻለው ይሁን እሺ. እውነታችሁን ነው ብሎ ወደኋላው ተመለሰ ። ግራኝ አህመድ ባለፈው ሁሉ እንደ ተገነዘብነው መረዳትን የሚፈልግ ምክር ሰሚ መላንና ዘዴን የሚያመዛዝን ደንበኛ መሪ እንጂ በበላይነቱና በሥልጣኑ ማናቸውም ሥራ እንዲፈጸም የሚያስገድድ አለቃ አልነበረም ። ድልን አከታትሎ የሰጠው የዚህ ዓይነት የመሪነትና የትዕግሥት ጠባዩ ነው ። በእልሁ የማይገዛ እልሁን የሚገዛ ሲመቸው የሚያጠቃ ሳይመቸው የሚሸሽ በመሆኑ ምክርን ሁሉ መስማት ከዚያም ውስጥ የተሻለውን የመምረጥ ችሎታና ስጦታ ስለነበረው አሁንም የነገሩን አዝማሚያ በማመዛዘን ወደ ፊት ሲመቸውና አዲስ ዝግጅት አድርጎ በሚቀጥለው ጊዜ መመለሱ ላይቀር አሁን ለጊዜው የአምባ ግሺንን ውጊያ ትቶ ወደ ሐይቅ ደሴት ከዚያም ወደ ሸዋ መመለሱን እንመለከታለን ።

ISIC

## ምዕራፍ ፳፯

### የግራኝ ወደሸዋ መመለስና ሞተ ተብሎ ስለመወራቱ — በደብረ ብርሃን የግራኝና የወዚር አዶሉ በታላቅ ሰልፍ መገናኘት — በዚያን ዘመን ወርቅ ስለመርከሱ (፲፭፻፳፬ - ፲፭፻፳፭ ዓ. ም.)

ባለፈው ሁሉ ያነበብነው የሚያስታውሰን በዋስል (የዛሬ ወረይሉ) ላይ ከተሸነፉ በኋላ ባሁን ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል አምባ ግሼን ላይ የጦር አለቆቻቸው እነቢትወደድ ሠርፄ ባስገኙላቸው ድል ተጽናንተው በቤገምድር ግዛት ውስጥ መገኘታቸውን ነው ። ግራኝ አህመድ ግን በአምባ ግሼን ጦርነት በኅዳር ወር ከዋናኞቹ ጦር መሪዎቹ ውስጥ አማቹ ማታን ከሞተበትና ገራድ አህሙሽ ከተማረከበት ወዲህ አምባ ግሺንን ሳይበቀል ንጉሡንም የመከታተሉ ጉዳይ ለጊዜው እንዳልተቻለው ተመልክቶ ራሱ ወደ ሐይቅ በታኅሣሥ ወር መጥቶ በሐይቅ የሚገኘውን ሀብት ከመምህሩ ተስማምቶ በሙሉ እንደ ወሰደ ገዳሙን ግን በውሉ መሠረት ሳያቃጥል እንደተወው አንብበናል ።

ጦርነት ከገጠመረ እንሥቶ በፈቃዱ ሳያቃጥል የቀረው ይህን መካነ እስጢፋኖስ የሚባለውን ገዳም ብቻ ነው ። ይህም ገዳም ከመቃጠል የተረፈው ያገሩ ሰው ሐርብ አራድ ስለአማለደ ለእርሱና በእርሱ አማካይነት ለመምህሩ የሰጠውን ቃል ለማክበር ይሁን ወይም በአምባ ግሼን ጦሩ ከተመታበት ወዲህ ገዳሙን በማቃጠል ያገር ተወላጆቹ ሳይዓቅ ተቀስቅሶ ጦሩን እንዳይጐዳበት ይሁን አይታወቅም። ወይም ሁለቱን በማመዛዘንና ሀብቱን ካገኘሁ ለጊዜው ይበቃል ብሎ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ሐይቅን ከበዘበዘ ወዲህ ወደ ዋስል ተመልሶ ከዋስል ወደ ግድም ከግድም ወደ ደብረ ብርሃን (ሸዋ) መጥቶ ለደቡቡ ክፍል ዋና የበላይ አስተዳዳሪና ጠባቂ አድርጎ ከተወው ከወዚር አዶሌ ጋር በሰልፍ መገናኘታቸውን በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን ። ግራኝ አንድ ከፍ ያለ ድል ካገኘ በኋላ በዚያው በመቀጠል ፈንታ ሁል ጊዜ ወደኋላው ተመልሶ አዲስ ዝግጅት ማድረግ ልማዱ ነው ። ባለፈው ጊዜ ከአይፈርስ ጦርነት ከሽምብራ ኩሬ ድል በኋላ ወደ ሐረር ሄዶ እንደገና ተዘጋጅቶ መመለሱን እናስታውሳለን ። አሁንም የአማራን ግዛት ከወረረና ከዘረፈ በኋላ ሀብቱን አስጭኖ ሠራዊቱን እንዳስከተለ የላስታንና የትግሬን ወረራ ለሌላ ጊዜ መድቦ ወደኋላው ወደ ሸዋ ተመለሰ ።

ነገር ግን ይኸ ሁሉ ሆኖም ሥልጣኔን አስፋፍቻለሁ ሕዝቡን አስገብሬ እስላማያለሁ በሚለው በዚሁ በደቡቡ አገር ለጠላት አንገዛም ፡ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን አንተውም ብለው እስከመጨረሻ ሊዋጉ የቆረጡ የጦር አርበኞች ገና አሉ ። ከነዚህም ዋንኞቹ የደብረ ብርሃኑ (ተጉለት) አዛዥ ጊዮርጊስ (ተክለ ጊዮርጊስ) የባሌው አዝማች አዳሉ ፡ የወጅ እስላም ደሀር ዮናዳብና ፋኑኤል ናቸው ።

ዓረብ ፋቂህ በዚሁ መጽሐፍ ላይ ግራኝ አህመድ ስመ ጥሩውን የእስጢፋኖስን ገዳም ከበዘበዘ በኋላ ፈጠጋር ላይ ከተወው ከወዚር አዶሌ ጋር ለመገናኘት ከሐይቅ ተንሥቶ ዋስል ላይ መስፈሩን እዚህም በሠፈረበት ሰዓት በዘረፋ ከከበ

ሩት ሹማምንቱ አምስተኛውን እጣ አምጡ ብሎ ተቀብሎ ከዋስል ወደ ጐጀማህ ከዚያ ወደ አብሽሎ ዘራፍ መድረሱን በዚያም ሳለ መካነ ማርያምና ደብተራ ማር ያም የሚባሉ (1) አብያተ ክርስቲያናት ከዘረፋ የተረፉ አሉ ማለትን ሰምቶ ወደ ኋላው ተመልሶ እነዚህን አቃጥሎ ወደ ሠፈሩ ከተመለሰ በኋላ ከዚህ በፊት በግድ ሰልሞ የነበረው አይበስ ለሐዬ ካንድ እስላም ከሚባል ጋር ከሠፈር አምልጠው ወደ ንጉሣቸው መሄዳቸውን ከዚያም ግራኝ ወደ ጋንቡራ (ግድም) በመጣ ጊዜ ዋርጀይ አቡን የሚባል የዘይላ ባላባት ገጸ በረከት ይዞ መጥቶ የሐረርጌንና የአዳ ልን አገር ወሬና ደህንነት አዶሌም የሚገኘው በፈጠጋር መሆኑን እንዳጫወተው ቀጥሎ ገራድ ኡስማንን ሹፍረ ጨምሮ ደብረ ብርሃን ላይ እንገናኝ ብሎ ለአዶሌ እንዲነግረው መላኩንና ራሱ ግራኝ ግን ከግድም ወደ መንዝ አልፎ መስፈሩን ይጽ ፋል (2) ።

ከዚሁ አያይዞ የዓረቡ ጸሐፊ ግራኝ አህመድ ቤተ አምሐራ እነዚያን አብያተ ክርስቲያናት ለማቃጠል ሂዶ በነረመበት ሰዓት አዝማች ፋኑኤልና አርኪያህ የሚ ባሉ የክርስቲያን ሹማምንት ከአውራይ ኑር አዋስ ጋር ተዋግተው ከእስላሞቹም ብዙ ሰው ከሞተ በኋላ ክርስቲያኖቹ መሸነፋቸውን ። ቀጥሎም ከአዝማች አዳሉ ጦር ውስጥ አንዱን ክፍል በሩቁ አይተው እስላሞቹ ሲያባርሩ ጨለማ ገላግሏቸው መመለሳቸውን ከዚያም ዮናዳብ ከሚባል ከወጅ ሹም ጋር ተዋግተው በዚህ ጦር ነት ዘሐርቡይ ኡስማንና ዮናዳብ ብቻ ለብቻ[illegible]ጥመው ሲዋጉ እስላሙ በጦር ክርስቲያኑን ወግቶ እንደገደለው ፤ እንደዚሁ አድርጎ ዘሐርቡይ ኡስማን ከክርስቲ ያኖቹ የዘረፈውን ዕቃ አዋሽ ወንዝ ዳር ቆሞ ሲያሻግር አንድ የማያ (አሩሲ ውስጥ) ሰው በዛፍ ውስጥ ተደብቆ በቀስት እንደገደለው በዚያን ጊዜ አለቃቸው ሲሞት የቀሩት እስላሞች በሽሽት ወደ አዶሌ መሄዳቸውን ጨምሮ ይጽፋል ።

ስለዚህ ከመሰን ሰገድ ሞት ወዲህ ንጉሡም ወደ ቤተ አምሐራ ከሄዱ በኋላ በተወረረው በደቡቡ ግዛት ግማሹ በፍርሃት እየተገዩ ቢገዛም ቢሰልምም ግማሹ እንገዛም እያለ ብዙ ጊዜ የግራኝን ጦር በያለበት እየተዋጋ ትግሉን ከመቀጠል አላ ረፈም ። ብዙ ጊዜ ተዋጉ የሚላቸው የኤል ማያን ሰዎች ነው ። ሹማቸውንም በአ ሁኑ ሰዓት ዮናዳብ የወጅ ሹም ይለዋል (3) ። የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ሌላውም ሰነድ ሁሉ ከአዋሽ ወደ ሰሜን ያለውን የዛሬውን የየረር የቡልጋን የምንጃርን ግዛት ፈጠጋር ይልና ከአዋሽ ወደ ደቡብ ያለውን የዛሬውን ማረቆን የዚያን ዙሪያ ሁሉ በዚያን ጊዜ አጠራር ወጅ ይለዋል ። የዛሬው የሱካር ፋብሪካ ያለበት ወንጅ ከዚያ የመጣ ስም መሆን አለበት ። ሕዝቡንም እንደዛሬ አሩሲ ፤ ማረቆ ሳይል የኤል

(1) መካነ ማርያምን ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ደብተራ ማርያምን ልጃቸው በእደ ማርያም የአሠሩዋቸው ናቸው ። የዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ገጽ 132

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 338 - 339

(3) ዮናዳብ የንጉሡን የወንድም ልጅ የዮሐንስን ልጅ ያገባ ያደርገዋል ። በዚህ ላይ የወጅ ሹም ሲለው በሌላ ቦታ ላይ በጠቅላላው የወጅ ሹም የሚለው እስላም ደሀር የሚባለውን ነው ። ምናል ባት የበላይና የበታች ይሆናሉ ።

ማያ ሕዝብ እያለ በቀስት ውጊያ በዝቋላ ዙሪያ ያደረጉትን ጦርነት ከዚህ ቀደም ያደነቀውን እናስታውሳለን ።

የሆን ሆኖ በዚሁ ጊዜ ክርስቲያኖቹ ከመሣሪያው ጦርነት ጋር የገቡትም ያልገቡትም ክርስቲያኖች በግራኝ ላይ የሞት ወሬ እያወሩ የግራኝ ጦር እንዲሸበርና ወዳገሩ እንዲሸሽ በያለበት የስብከት ጦርነት ያደርጉ እንደነበረ በዚህም ስብከት ለተያዘው ለደቡቡ ክፍል ጠቅላይ ገዥ ያደረገው አዶሌና እስላሞች ሁሉ በታላቅ ሥጋት ላይ ወድቀው ሳሉ በኋላ ግን ወሬው አሰት ሆኖ ግራኝና አዶሌ በታላቅ ሰልፍ ደብረ ብርሃን ላይ በደስታ መገናኘታቸውን ከደስታ ብዛት የተነሣ ግራኝ ማልቀሱን ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ እያለ ይተርካል ።

«ወዚር አዶሌ በዚህ ሰዓት የነበረው ሞጃ (ሞጆ) ነው ። በዚሁ ጊዜ ይማም አህመድ ከአበሻ ንጉሥ ጋር ጦርነት ገጥሞ እስላሞቹ አለቁ የሚሉ አሰተኛ ወሬ ለወዚር አዶሌ መጣለት ። ይኸም ሲሰማ በእስላሞቹ ሁሉ ዘንድ ታላቅ ኀዘን ሆነ ። በፍርሃትና በግዴታ እስላም እየሆነ ከነርሱ ጋር ያለው ክርስቲያን ግን ደስታ ተሰማው ። ወሬውንም ያመጡት እነሱው ናቸው ። ወዚር አዶሌ ሲጠይቃቸው "ጦሩ ተሸንፎ አልቆበት ይማም ጥቂት ወታደሮቹን ይዞ አመለጠ" ብለው ክርስቲያኖቹ ነገሩን ይሉታል ። ከርሱ ሲለዩ ይማም ከነጦሩ አለቀ እያሉ ሁለት የሐሰት ወሬ አስወሩ . . . . . ብዙው አብሮት ያለው እንዳይሞት ለነፍሱ ሲል በቅርብ ቀን የሰለመ ሕዝብ ብቻ ነው ። ከወዚር አዶሌ ጋር ከአዳልና ከሱማሌ አገር የመጣው እውነተኛው እስላም ጥቂት ነው ።

ስለዚህ የዚህን ወሬ ከሰማ በኋላ ወዚር አዶሌ ኤሚር ሁሴንን ፣ ገራድ ፋንጃናትን ፣ ኤሚር ዲንን ፣ ገራድ አህመድን ፣ ኤሚር ሻሙን ፣ የጦር ሠራዊቱን ሱማሌውንም ሁሉ ሰበሰበና "ይማም እውነት ሞቶ እንደሆነ አንድ ሰው ጉደለ ማለት ነው ። ጥንቱን ከአገራችን የወጣነው ቅዱስ ጦርነት ለማድረግ ነው ። በመካከላችን የክርስቲያኖች ሰላይ ወይም ግብዝ ሰው እንዳለ ይናገር ወይም ወደ ንጉሡ ይሂድ ። ምንም ቢሆን ይማም ሳይመጣ ጦርነቱን ሳንፈጽም ወደ አገራችን አንመለስም ። እርሱ ሞቶም እንደሆነ አንድ ሰው ነውና ጦርነቱን ለመቀጠል እኛው እንበቃለን" ብሎ (ዲስኩር) ተናገረ ።

ከዚያ በኋላ ወዚሩ ይማም የሚገኝበትን አገር ሰልል ብሎ ኤሚር ሑሴንን ወደ ኩዌዝ ወደ ዋራባህ ላከውና ኤሚሩ ከዋራባህ ሁለት የክርስቲያን ባላገሮችንና አንድ ረኸርም ወታደር ማርኮ ወደ ወዚር ተመለሰና አቀረባቸው ። ወዚር አዶሌም ይማም የሚገኝበትን ሥፍራና ስለንጉሡም የሚያውቁትን እንዲናገሩ ቢጠይቃቸው ይማም ወደ ዋስል ሄዶ ከደገልሃን ተጋጥሞ ነበር ። ከዚያ ደግሞ በድንገት ወደ ንጉሡ ገሥግሦ ሄዶ ጦርነት ገጠመና ንጉሡን አባረራቸው ብዙ ክርስቲያኖችም ሞቱ ብለው መለሱለት ይኸን ሲሰሙ እስላሞቹ ሁሉ ደስታ አደረጉ ።

ከዚህ በኋላ ወዚር አዶሌ እናንተ ጓዝ ጠብቁ እኔ እስከ ደብረ ብርሃን ድረስ ሄጄ ስለይማም እውነተኛውን ወሬ አጣራለሁ ብሎ ለኤሚር ሑሴንና ለገራድ ፋንጃናት ነገረና ወደ ደብረ ብርሃን ጉዞውን ጀመረ ። በሚጓዝበትም ጊዜ ከርሱ ጋር የነ

በረውን ገራድ ሻሙንን አንተ በታችኛው በኩል አድርገህ ሄደህ ደብረ ብርሃን ላይ እንገናኝ ብሎ ታቹን ላከውና እርሱ ቀድሞ ደብረ ብርሃን ገባ ። እስላሞቹ በቀኙና በግራ እየተከፋፈሉ አገር እየፈተሹ ክርስቲያንም ሲያገኙ ይዋጉ ነበርና በዚሁ ጊዜ ያንድ ክፍል የእስላም ጦር ከደገልሃን በታች ሆኖ ባሌን ይገዛ የነበረውን አብርሃም የሚባለውን አግኝተው ተዋጉት ። አብርሃም የዋስል ጦርነት ለት ክርስቲያኖቹ ተበትነው ሲሸሹ እርሱ ወደባሌ መጥቶ ነበር ። አሁንም ከእስላሞቹ ጋር እንደ ግጭት ከተገናኘ ወዲህ እርሱ ስለአመለጠ ከርሱ ጋር የነበሩት አሽከሮቹ ተያዙና ለምርመራ ወደ ወዚር አዶሴ አቀረቡዋቸው ። በተጠየቁም ጊዜ ይማም ንጉሡን አሸንፎ አባሯል ። ብዙም ክርስቲያኖች ገድሎ ፈረሶቻቸውን ቀምቷል ፤ እስላሞቹ ግን ምንም አልሆኑም ብለው ስለመለሱለት በእስላሞቹ ሠፈር ደስታ ሆኖ አደረ ።

ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ንጉሡ በደዋሮና በባሌ ያለውን ጦሩን አንድነት ሆና ችሁ ወዚር አዶሴን ውጉ ብሎ ትእዛዝ አስተላልፎላቸው ነበር ፡ አሁን ግን አዶሴ ስለይማም ይኸን እርግጠኛ ወሬ ከሰማ በኋላ ወደ ፈጠጋር ወደ ሠፈሩ ተመለሰ ። ገራድ ሻሙን ጉዞውን ታቹን ቀጥሎ ደብረ ብርሃን ቢደርስ ወዚር አዶሴን ሳያገ ኘው ቀረ ። ነገር ግን በርሱ ፈንታ ጊዮርጊስ የሚባለውን የክርስቲያኖች የጦር አለቃ ከብዙ ወታደር ጋር አገኘው ። ስለዚህ የሁለቱም ወገን ወታደር ለውጊያ ተሰለፈና ጦርነቱን ዠመረ ትልቅ ውጊያም ከሆነ በኋላ አበሾቹ ሸሹ ። እስላሞቹም ተመልሰው ወደ ወዚር አዶሴ ሄዱ . . . . . ። በዚህም ጊዜ ከይማም ዘንድ ወደ ወዚር አዶሴ የተላኩት ገራድ ኡስማንና ድል ሰገድ . . . . . . እመንገድ ደክመው ቆይተው በኋላ . . . . . . ወዚር ዘንድ ደረሱና ይማም የሀበሻ መንግሥት ጌታ ነው ። ንጉሡን ከነመኳንንቱ አሸንፎ አባረራቸው ንጉሡም ያመለጠው በስንት ችግር ራሱ ብቻ ነው ። እስላሞቹ ከጠላት ጋር የነበሩትን ሴቶች ሁሉ ማረኩ ሥፍር ቁጥር የሌለውን ወርቅ ፡ ብር ፡ የሐር ልብስ ወሰዱ ። ይማምም አንተን ደብረ ብርሃን ድረስ እንገናኝ ብሎሃል ብለው ስለነገሩት ነጋሪት እየተመታ መለከት እየተነፋ ታላቅ ደስታ ተደረገ ።

ከዚህ በኋላ እየተጓዘ ደብረ ብርሃን ደርሶ ይማምን ይጠብቅ ዠመር ። ይማም በዚህ ሰዓት መንዝ ነበርና ይኸን ወሬ ከሰማ በኋላ ከመንዝ ወደ ተጉለት መጥቶ ቅዱስጌ አደረ (1) ። ከዚያ ይኸው ባንተው አቅራቢያ ሠፍረናል ብሎ ለወዚር ቢልክበት የፈረሰኛውንም የእግረኛውንም ጦር ነገዱንም ሁሉ በደንብ አሠልፎ ወዳንተ እንድመጣ ትእዛዝህ ይድረሰኝ ይኸንንም ማለቴ በመካከላችን የክርስቲያ ኖች ሰላይ አለና ያለንበትም የክርስቲያኖች አገር ስለሆነ ኃይላችንን እንዲያዩ ብዬ ነው ብሎ መልስ ወደ ይማም ላከ ። ይማምም ጥሩ አሳብ ነው ብሎ አዶሴን አደነ ቀው ። እርሱም በበኩሉ አዶሴ ሊመጣ ነው ተዘጋጁ ብሎ ከርሱ ጋር ያሉትን ሹማ ምንቶችና ወታደሮች ፈረሰኛውንም ሁሉ ከክርስቲያኖቹ ላይ በተማረከውና በተዘረፈው ዘውድ ወርቅና ብር የሐር ልብስ የወርቅና የብር ካባና ቀሚስ የራሱን

(1) ቅዱስጌ ያለው በቡልጋ ውስጥ ነው ። ወይስ በተጉለት ሌላ ቅዱስጌ ይኖር ? ወይስ ቡልጋ በዚያን ጊዜ የተጉለት ክፍል ይሆን ?

ዘበኞቹንም ከባሕርና ከዓረብ አገር የመጡትን ከአለቃቸው ከሻምሱ ጋር አሳምሮ አልብሶ አስጊጦ ሲጓዝ ፣ ወዚሩ በጦሩ ማህል ሆኖ ብቅ አለ ። ጦሩ ፱ ላይ ተከፍሎ እያንዳንዱ ክፍል ባንድ አንድ ገራድ ወይም ኤሚር ይመራ ነበር ። እነዚህንም ሁሉ በ፫ ረድፍ አሰልፏቸው ሲመጣ ከሰው ብዛት የተነሣ የሠልፈኛው ጫፍ አይ ታይም ነበር ።

በዚህ ቀን ወዚር አዶሌ ያሰለፈው የፈረሰኛ ጦር ፫ሺ ጥሩር የለበሰ ፣ ፫ሺ ጥሩር የሌለው ፣ ፳ሺ ባለነጭ ጋሻና ጦር እግረኛው ይኸንኑ ያህል የቀስተኛውም ጦር እንደዚሁ ነበር ። ከይማም ጋር የነበረው የፈረሰኛ ጦር ፭ሺ ነው ። እነሱም በወርቅ ያጌጠ ልብስ ለብሰው ጥሩራቸው ካይናቸው በቀር ሌላውን መልካቸውን ሸፍኖት አይታይም ነበር ። በራሳቸው ላይ የደፉትም እንደመስተዋት ያበራ ነበር ።

የወዚር አዶሌ የጦር ሠራዊት ከአለቆቻቸው ጋር ሆነው ሱማሌን ይዘው ፈረ ሰኞቻቸው እይማም ፊት ሲደርሱ ሰላምታ ሰጥተው አለፉና ወደጐን ዞረው ቆሙ ። ሁለተኛው ክፍል የፈጠጋር የማያ የሸዋና በቅርብ የሰለመው ነገድ ተሰልፎ በግራኝ ፊት ቀርቦ ሰላምታ ሰጥቶ አለፈና በመዠመሪያው መስመር ጐን ቆመ ። በ፫ኛው ክፍል ውስጥ ወዚር አዶሌ ፣ ኤሚር ሁሴን ፣ ኤሚር ሻሙን ፣ አውራይ ጉር ፣ ኤሚር ዲን በጠቅላላው ፱ የሚሆኑ የጦር አለቆች ብዙ ጦር ይዘው ከወታደሩ ብዛት የተነሣ የሰልፋቸውን መስመር ሳይለቁ እይማም ፊት ደረሱ ። ሥፍራውም ጠቦ ነበር እነሱንም በየተራ ሰላምታ ሰጥቶ ሲአነጋግራቸው ይማም የደስታ ለቅሶ አለቀሰ ። ከነርሱም ከተለያየ ሰባት ወር ሆኖት ነበር ከድዙ ኤል ሂጂጃህ ፱፻፴፯ - ፱፻፴፰ - የጁማዳ (1) ።

ይማም ከግምጃ ቤቱ እያስመጣ ወርቁን ብሩን የሐሩን ልብስ ከአዶሌ ጋር ለነ በሩት የእስላም የጦር ሠራዊት ለ፱ የጦር አለቆቹ ለያንዳንዱ ጥፍጥፍ ወርቅ ሰጠና ለቀረው ወታደር እንደየድርሻው ወርቁንም ብሩንም የሐሩንም ልብስ አከፋፈ ለው ። በእስላሞቹ ዘንድ ወርቅ በጣም ተትረፈረፈ ። ሰው ሁሉ የሚገበያየው በወ ርቅ ሆነ ። ከእስላሞቹ ዘንድ አንዱ አንድ ነገር ሲያስፈልገው ወርቅ በእጁ ይዞግንና ወደ ገበያ ሄዶ በወርቅ ገዝቶ ሸቀጡን ይዞ ይመለሳል ። ከብዛቱና ከመበርከቱም የተነሣ ወርቅ መመዘን ቀረ ። ያንድ በቅሎ ዋጋ አርባ ወቄት ወርቅ ደረሰ ። አንዱ ወዳንድ ወዳጁ ዘንድ ሊጐበኘው ሲሄድ ተጐብኚው አለቃ እንደሆነ ብር ሲያቀርብ ለት ይኸን የምትሰጠኝ ፩፻ ወይም ፪፻ ወቄት ወርቅ አጣህና ነውን ብሎ አልቀበ ልም ይላል ፱ ወቄትም ወርቅ ሲሰጠው አነሰኝ እያለ ይቆጣል ይኸ ሁሉ ሀብት የተገ ኘው ከቤተ አምሐራ ነው ። የወርቅና የብር ብዛት እንደቤተ አምሐራ በአበሻ ሀገር በየትም የለም» ሲል ዓረብ ፋቂህ አሳቡን ይደመድማል (2) ።

ዓረብ ፋቂህ በጽሑፉ ውስጥ እንደዘመኑ ጸሐፊ ሁሉ በአተራረኩ የወገኖቹን

(1) ሬኔ ባሴት እንደ አው. ቍጥር 1531 - 1532 ያደረጉት በኛ ቍጥር ፲፭፻፳፬ ነሐሴ ፲፭፻፳፭ የካቲት ይሆናል ።
(2) ዓረብ ፋቂህ 338 - 354

የእስላሞቹን ገነን የክርስቲያኖቹን ኰሰስ እያደረገ የክርስቲያኖቹ ጸሐፊዎች እንደሚያደርጉት መጻፉ አልቀረም ። አንዳንድ ጊዜም ፲ እስላም ከ፻፶ ክርስቲያኖች ተጋጥመው አሸነፉ ይላል ። ባንዳንድ ሥፍራ ላይ ትልቅ ጦርነት ተደርጎ ከክርስቲያኖቹ ፫፻፶ ሰው ሲሞት ከእስላሞቹ ፫ ሰዎች ሞቱ፡ አንዳንድ ጊዜም ምንም አልሞተም እያለ ያልፋል ። ደግሞ አንድ ክርስቲያን ሹም ከአንድ የእስላም ሹም ጋር በፈረስ ወይም በእግር ብቻ ለብቻ በሰይፍና በጦር በትር ተማትተው እስላሙ ያሸነፈ እንደሆነ "የኛ ዠግናው እስላም ጣዖት አምላኪውን ክርስቲያን በሚያስደንቅ አኳኋን መትቶ ከፈረሱ ገልብጦ ገደለው የሚቸም ነፍስ ወደ አሳዛኙ አገር ወደ ሲዖል ትውረድ . . . . . ." ይላል ። ክርስቲያኑ እስላሙን ሲገድለው በሰማዕትነት ሞተ ነፍሱ ወደ ገነት ትውጣ ይላል ። ይህን በመሳሰለ ነገር ከመለያየቱ በቀር በተረፈ የዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ እውነተኛ ነው ። በተቻለው ሐቅም ለመከተል ሲፈልግ በእስላሞቹ ላይ የደረሰውን መሸነፍ አይደብቅም ። ከክርስቲያኖቹ አለቆች ውስጥ የነጸሐፈ ላም ሮቤልን ይልቁንም የልጁን የአዝማች አምዱን (ዓምደ ሚካኤል) የአዝማች ተክለ ጊዮርጊስን ዠብዱ አጋንኖ ገልጿል ። ወደፊት ደግሞ በባሌ የገርግናውን የአዝማች አዳሉን አርበኝነትና ዠግንነት በደንብ ይተርክልናል ።

እንደዚሁም ስለወርቅ መርከስ የጻፈው ከእውነት አይዘልም ። በኛም በኩል ያለው ታሪክ ነገሥት በዚህ ዘመን ወደፊት ከምናነበው ከላስታና ከትግሬ ጦርነት ከግሼን አምባ ዘረፋ በኋላ ያለውን የወርቅና የሐር ልብስ መርከስ ሲያስረዳ «በዚያን ጊዜ ወርቅ እንደ ደንገያ የሐር ልብስ እንደቅጠል ረከሶ ያንድ ወቄት ወርቅ ዋጋ ፴ አሞሌ ጨው ያንድ ወቄት ወርቅ ዋጋ አንድ በሬ ሆነ» ያለውን በሥፍራው ስንደርስ እንገነዘባለን ። ወርቅና ብር የሐር ልብስ እንደዚህ መርከሱን በአድናቆት ዓረብ ፋቂህም ታሪከ ነገሥቱም ሲተርኩልን ሁለቱም ካሁኑ ሁኔታ ጋር ለማመዛዘን እንዲመቸን የቀድሞውን የገበያ ዋጋ በሙሉ ሳይሆን ለምሳሌ ያህል እንኳን አልጠቀሱልንም ።

የሆነ ሆኖ እስከዚህ ወርቅና የሐር ልብስ ከመርከስ የደረሰበት ምክንያት ለማንም ሥውር ሊሆን አይችልም ። ከላስታ መንግሥት ወደሸዋ ከዞረበት ከ፲፪፻፷፪ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ አሁን እስከ ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ፮፻፺፱ ዓመት መሆኑ ነው ። ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ በድምሩ ፳፱ ነገሥታት አልፈዋል ። ጥቃቅኖቹን እነ ባሕር አሰግድን እነጽንፈ አሰግድን ወደ ጐን ብንተዋቸው የቀሩት እንደ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ፣ እንደ ሠይፈ አርዕድ ፣ ዓፄ ዳዊት ፣ ዓፄ ይስሐቅ ፣ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፣ ዓፄ በዕደ ማርያም ፣ እንደ ዓፄ እስክንድር ፣ እንደ ዓፄ ናዖድ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በመትከል ገዳም በመገደም ገዳማቱንና አብያተ ክርስቲያናቱን በስጦታ በስለት ለማክበር የሚጣጣሩ ፣ እኔ ልብለጥ ወይም የኔ ይብለጥ በማለት የሚፎካከሩ መሆናቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

እነሆ ከነርሱ በፊት በላስቶቹ ሳይቀር በተለይ ደግሞ በነዚህ ነገሥታት ጊዜ በወርቅና በብር ፣ በሐር ልብስ የደለቡት የቤተ አምሐራ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት አሁን በግራኝ አህመድ ጊዜ እየተበዘበዘ የተዘረፈውን መጠኑንና ሁኔታውን

ለመገመትና ለማስታወስ ያህል ወዳለፉት ምዕራፎች አሳባችንን አንድ ጊዜ እንመ
ልስ ።

፩ኛ. ስለመካነ ሥላሴ አዘራረፍ ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ብሏል "..... ግራኝ እመካነ ሥላሴ ቅጽር አጠገብ በደረሰ ጊዜ ቆም ብሎ ከጓደኞቹ ጋር ቤተ ክር ስቲያኑን እያየ አደነቀና ወደ ውስጥ ገባ ። በወርቅና በብር ያጌጠች ቤተ ክር ስቲያን ናት ...... በዚያን ጊዜ ሺ የሚሆኑ እስላሞች ሺ መጥረቢያ ይዘው ወርቁንና የከበረውን ደንጊያ እየፈነቀሉ ሲያነሡ ከ፲ ሰዓት ዠምሮ እስከ ማታ ድረስ ጊዜ ወሰደባቸው ......"

፪ኛ. አትሮንስ ማርያም ወዚር ኑር የአስዘረፈው ለት መቶ ሰዎች ወደ ዕቃ ቤቱ ገብተው እያወጡ ቢያከማቸው ቁሜ ማለታቸውን ዓይቶ አሊቃቸው ምነው ቁሜ አላችሁ አለቀ እንዴ ቢላቸው ዕቃው እንዳለ ነው እኛ ግን ደከመን አሉት ..... ከዚያ ቢቸግረው "የከበረውን ልብስ ማጋዝ ተዉና ወርቅ ብቻ አግዙ ብሎ አዘዘ ...... ማጋዙ እስከ ማታ አላልቅ ስላለ ለማጋዝም ከብት ስላነሰ ለክርስቲያኖቹ እንዳይተርፍ ተብሎ የወርቁን ዕቃና ልብስ ከነ ቤተ ክርስቲያኑ አቃጥሉት" አለ ...... ።

፫ኛ. አብድ ኢንናስር የሚባለው ገነተ ጊዮርጊስን ካቃጠለ በኋላ "ሁለት የንጉሡ ግምጃ ቤቶች የነበሩትን አግኝቶ አትግዩለን እንጂ የንጉሡ ወርቅ ብር ልብስ ፳፱ ሰው ለ፲፻፱ም የማይችለውን መርተን እናሳያለን ካሉት በኋላ በነርሱ መሪ ነት ዋላቅ ወደ ተባለው ሥፍራ ሄዶ በወርቅ የተጠለፈ ካባና ቀሚስ የወርቅ ማህንና ጥዋ ያሁኑና የቀድሞ ነገሥታት ብዙ የወርቅ ዘውድ ፣ በወርቅና በከ በረ ደንጊያ ያጌጠ የነገሥታቱ ልብስ ፡ የወርቅ መታጠቂያ እንባሩ ጩቤው ከወርቅ የተሠራው የበቅሎና የፈረስ ዕቃው ፣ ሁለመናው ወርቅ የሆነ ማህ ንና ስኒ ይኸን ሁሉ ዘርፎ ከመዘገበ በኋላ ለሦስት ሺ ሰው አሸክሞ ወደ ጌታው ወደ ግራኝ ሄደ ....." ።

፬ኛ. ሠይፈ አርዕድ ያሠራት የደብረ እግዚአብሔር ገዳም የተዘረፈች ለት በላዩ ላይ ያለው (የጨረሰው) ወርቅ ከብደቱ እንደተጻፈው ከጥፍጥፉ ከጥጆቹ በቀር 909.990 ወቄት ወርቅ ነው ...... ።

፭ኛ. በሐይቅ መካነ እስጢፋኖስ መምህሩ በውለታ የመነኮሳቱን ሕይወትና ገዳ ሙን ከቃጠሎው ለማዳን ሀብቱን በፈቃዳቸው ለማስረከብ ቃል ከገቡ በኋላ በግራኝ ትእዛዝ መሐመድ ዘሐርቡይ ወደ ደሴቱ ገብቶ ለማስጋዝ ፪ ቀን እን ደፈጀበት በጉድጓድና በጓዳ የተገኘውን የወርቅ መስቀል የወርቅ ሰንሰለት ከልክ ያለፈ የወርቅ ዕቃና ልብስ እግራኝ ፊት አምጥተው ሲዘረግፉለት ግራኝ ከሐይቅ ገዳም በወጣው ሀብት ተደንቆ በፊተኛው ጊዜ ያገኘውን ሁሉ እንደዘነጋው አንብበናል ።

ስለዚህ በዚህ ዓይነት ብዙ ዘመናት ደልቦ የኖረው ወርቅና ብር ራሱ ፡ ከወር ቅና ከብር የተሠራው የቤተ መንግሥት ዕቃና የቤተ ክህነት ንዋየ ቅድሳት ባንድ ጊዜ ተጉልጉሎ ወጥቶ ከዚህ በፊት ይኸን የመሰለ የወርቅ ሀብት ከማያውቁ ከግ

ራኝ መኳንንትና ሕዝብ እጅ ሲገባ ወርቁ ሆነ የሐሩ ልብስ እንደደንጊያና እንደ ቅጠል ረከሰ ቢባል አያስደንቅም ። የሚያስደንቀው በዚህ ሁሉ ሀብት የሀብቱ ባላ ቤቶች መሳፍንቱና መኳንንቱ ፣ ደሀና ባላገሩ ፣ ወታደሩና ነጋዴው ፡ በባለቤትነት ሳያጌጡበትና በምንም ዓይነት ሳይጠቀሙበት ብዙ ዘመን አልፎ በጠላት እጅ እን ዳለ መውደቁ ክርስቲያኖቹ ራሳቸው ባከማቹት ሀብት ግራኝና ሠራዊቱ በግማሽ ተጠቅመው በቀረው መሣሪያ እየገዙ እነርሱን ስለወጉበት ራሳቸው በገዛ ሀብታ ቸው ተመልሰው መጐዳታቸው ነው ።

በዚህ ላይ ያዕቆብ ሐዋርያ ለተበተኑ ለ፲፪ ወገኖች በጻፈው መልእክቱ ላይ «አሁንም እናንት ባለጠጎች ስለሚደርስባችሁ ሥቃይ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ ሀብታችሁ ተበላሽቷል ፡ ልብሳችሁም በብል ተበልቷል ። ወርቃችሁም ብራች ሁም ዝጓል ። ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል» ያለው በዚህ ዘመን በትክክል እንደደረሰ የሚቆጠር ነው (1)። የሐዋርያው ተግሣፅ በዚህ ዘመን የደረሰው በሀብት ራስን አለመጥቀም የጉዳቱ ትምህርት በማናቸውም ጊዜ ለማናቸውም ባለሥልጣን መምህር ነው ። ነገር ግን በምድር ያልተነገረ ፡ ያል ተጻፈ አይገኝም ። በተጻፈውና በተነገረው መማሩ ችግር ነው ። «ይሰበስባሉ ለማን እንደሚሰበሰቡ አያውቁትም» ብሎ ዳዊት የተናገረው ማንን አስተምሮ ያው ቃል ?። በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ትምህርቱም ፣ ዝንጋታውም ፣ መሰብሰቡም ፣ መዘ ረፉም እንደዚሁ በየፈራረቃ ሲቀጥል መኖር[illegible]ት ። ሁኔታው ይገርማል ።

በተረፈ በዚህ ምዕራፍ ላይ ክርስቲያኖቹወደ እስላሞቹ ሠፈር ሰላይ እየላኩ ማስመርመራቸውን የእስላሙ ጦር እንዲፈታ ግራኝ ተሸነፈ ወይም ሞተ ንጉሡ አሸነፉ እያሉ ማስወራታቸውን የወዚር አዶሌ ዲስኩር አስገንዝቦናል ። እኔ እንደ ሚመስለኝ ግራኝ ሞተ ተብሎ ከመወራት የደረሰው በአምባ ግሼን እነቢትወደድ ሠርጼ በግራኝ የጦር አለቆች በገራድ አህምሹና በገራድ ማታን ላይ ስለአገኙት ድልና ከዚሁ ተያይዞ ግራኝም ጦርነቱን ሳይቀጥል ፡ የወገኖቹንም ደም ሳይበቀል ወደፊት ገፍቶ ከዘለቀበት ከቤተ አምሐራ መዠመሪያ ወደ ሐይቅ ከዚያ ወደኋላው ወደሸዋ በመመለሱ ይሆናል ። ይኸም በክርስቲያኖቹ ዘንድ አውቀውም ሳያው ቁም ተሸንፎ ወደመጣበት ተመለሰ ወይም ሸሸ ብሎ ለስብከት ያህል ወሬው ተነ ዝቶ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከቤተ አምሐራ ተመልሶ በሸዋና በሸዋ ዙሪያ በደ ቡብ ኢትዮጵያ ያለውን ግዛት ከአደላደለ በኋላ ፣ ራሱም ባለፈው ባገኘው ድልና ሀብት እየተደሰተ ከሚስቶቹና ከቤተ ሰቡ ጋር አንድ ዓመት ያህል በሐድያ በወጅ በጉራጌ በፈጠጋር እየተዘዋወረ እረፍት ካደረገ በኋላ ባዲስ ኃይል ባዲስ ድርጅት ባመቱ በ፲፰፻፷፭ ዓ. ም. በሚያዝያ እንደገና ወደ ሰሜን ተመልሶ ለነአህሙሹ ያቃ ተውን አምባ ግሼንን ላስታንም ወርሮ ንጉሡን ልብነ ድንግልን ለመማረክ በግድ

(1) የያዕቆብ መልእክት ም. 5 ቍ. 1 - 4

ምና በቤተ አምሐራ በትግሬና በጸለምት በኩል አድርጎ ወደ ጐጃም መገሥገሡን ወደፊት እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፳፰

## የጀግናው የተክለ ጊዮርጊስና የራስ ነቢያት መከላከል (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ግራኝ አህመድ ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ጥቅምት ወር ዠምሮ እስከ የካቲት እነዚያን የቤተ አምሐራ አብያተ ክርስቲያናት ዘርፎ አቃጥሎ ወደ ደብረ ብርሃን መመለሱን አንብበናል ። ደብረ ብርሃንም በተጐለት ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥታቸው (፲፬፻፳፮ - ፲፬፻፷ ዓ. ም.) ያሠሩት በዚያን ዘመን የታወቀ ከተማ ነው (1) ። ግራኝ በቤተ አምሐራ እንደራሴው አዶሌ በደቡቡ ክፍል በፈጠጋር በነበሩበት ሰዓት እነዚህ በአርኤስቱ የተጻፉት የጦር አለቆች ሌሎችም (የወሰን ሰገድ ልጅ) የደፋሮው አዳሉ ፤ የባሌው ዮናዳብ ፤ የንጉሡ እማች የወጅ ሹም ፍቅረ ኢየሱስና ራስ ነቢያት ፣ ተክለ ጊዮርጊስ የተጐለቱ እነዚህ ሁሉ ለጠላት አንገዛም ብለው በያለበት ከግራኝ ጦር ጋር ትግላቸውን እንደቀጠሉ ናቸው ። እነዚህም ሁሉ የጦር አለቆች ስማቸውንና ዝግንነታቸውን በዚሁ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ የጨረፍታ ያህል ከማወቅ በቀር ሞላ ከጐደል የሕይወት ታሪካቸው በዚህ ጊዜ የሠሩትም ዝግንነት በዝርዝር ስለሌለ የበለጠ ልናውቃቸው ባለመቻላችን ያሳዝናል ።

ዓረብ ፋቂህ ተክለ ጊዮርጊስ የተጐለት ሹም (በተለይ የሾጀራሁ) ሲለው ከሌላ አውራጃ በሹመት ምክንያት ይምጣ ወይም የዚሁ ወረዳ ተወላጅ መሆኑን አይገልጽም ። ነገር ግን በውጊያው ላይ ከዚህ በፊት በእስላሞቹ ዘንድ የከበረውን ከቢር መሐመድን ስለገደለ በዚሁ የግራኝን ንዴት ዝግንነቱን እየጨማመረ እንደዚህ ሲል ይጠቅሳል ። «ይማም ሲሙን (ስምዖን) ወግቶ ከተመለሰ በኋላ . . . . . አብሳማ ኑርንና ኤሚር ሻሙንን ወደ ሾጀራህ (ወገራ ይሆን) ፰ሺ የእግረኛ ጦር አሲዞ ላካቸው . . . . . . የእግረኛ ጦር መስጠቱም አገሩ ለፈረስ የማይመች (ገደልማ) ስለሆነ ነው . . . . . ። እነሱንም ወደዚህ አገር ሲልካቸው የሾጀራህን አገር ሰጥቻችኋለሁ ነገር ግን የከቢር መሐመድን ገዳይ (የተክለ ጊዮርጊስን) ሙንቅላት ቆርጣችሁ ካላመጣችሁልኝ ከጀግና አልቆጥራችሁም አላቸው ። እነርሱም እንዲቀናን እግዚአብሔርን ለምንልን ብለው ሄዱ ። . . . . . . . ተክለ ጊዮርጊስ ከክርስቲያኖቹ ዝግኖች አንዱ ነው ። ጥሩ ፈረሰኛም ነው ። ብቻውን ከአሥር ፈረሰኛ ጋር ለመዋጋት የሚችል ሰው ነው ። እርሱንም ሻምሱ አንደኛውን በር አብሳማ ኑርና ገራድ (ኤሚር) ሻሙን ላይኛውን በር ይዘው ውጊያው ተዠምሮ ሲዋጉ ተክለ ጊዮርጊስ ወደ አንደኛው በር ሸሽቶ ለማምለጥ ቢደርስ ሳያስበው ከሻምሱ ጋር ተገናኘና

(1) የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 33

ሻምሱ ገድሎ ራሱን ቆርጦ ለአህመድ (ግራኝ) አመጣለት ፡፡ ይማም ባየው ጊዜ ትልቅ ደስታ ተሰማው ፡፡ ጭንቅላቱንም ላመጣለት ለሻምሱ የወርቅ አምባር የሽልማት ልብስ ሰጠው» (1) ፡፡

ከቢር መሐመድ ከዚህ በፊት እንደምናስታውሰው ግራኝ አህመድ በሸዋ ዙሪያ ያለውን አገር ወርሮ ሲጨርስ ራስ ወሰን ሰገድም ከሞተ በኋላ ወደቤተ አምሐራ ሲገዝ ይህ በኋላችን ያለውን የክርስቲያን አገር ከገበረና ከሰለመ ቅርብ ጊዜ ነው ፤ አሁን ትተነው ስንሄድ ወደቀድሞ ሃይማኖቱ ይመለሳልና እኔ ወይም ሻምሱ መቅረት አለብን ብሎ ለግራኝ ያማከረና ግራኝ እውነትህ ነው አንተው ቅር ብሎ መርቆ አሰናብቶ ያስቀረው ነው ፡፡ ከዚያም ወደ ወረባ ሄዶ ዓፄ እስክንድር ባሠራት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከማቸውን ወርቅ ለመዝረፍ ሲል ከአገር ተወላጁ ጋር ሲዋጋ መሞቱን ከዚህ በፊት እንደአነበብነው ያገር ተወላጁ መሪና ጎዳዩ በዚያ ላይ ስሙ ያልተገለጸው የተጉለቱ ተክለ ጊዮርጊስ ኖሮአል ፡፡

እንግዲህ ግራኝ ቤተ አምሐራ በነበረበት ሰዓት ተክለ ጊዮርጊስ በተጉለትና በዙሪያው በገደላገደሉ አገር (ምናልባት በመራቤቴ ፤ በጐላ ፤ በአንኮበር ዙሪያ) እየተከላከለ የግራኝን ሹማምንት ግማሹን ሲገድል ቆይቶ ሳለ አሁን ግራኝ ደብረ ብርሃን ተመልሶ ከአዶሌ ከተገናኘ በኋላ እርሱ በሌለበት ሰዓት ጦሩን ያስቸገሩበትን ወዳጁን ከቢር መሐመድን የገደሉበትን ክርስቲያኖች በአዲስ ኃይል አዳዲስ የጦር ሠራዊት እየላከ ያስወጋል ማለት ነው ፡፡ ISIC

ደብረ ብርሃን የገባለት ከአዶሌ ጋር ተሠልፎ በግራኝ ፊት ሰላምታ እየሰጠ ያለፈውን የጦር ብዛት ዓረብ ፋቂህ ገልጾታል ፡፡ በዚያም ውስጥ ከአዳሉ ፤ ከሱማሌው ከዓረቡ ይልቅ በቅርብ ጊዜ የገባለት የደፋቱ የደዋሮው የፈጠጋሩ የሸዋው የአማራው ሕዝብ እንደሚበዛ የታወቀ ነው ፡፡

በኢጣልያ የወረራ ጊዜ ቊጥራቸው ያነሰ የኢጣልያ ተወላጆች ቊጥሩ የበረከተውን ያገር ተወላጅ ባንዳ በሚል ስያሜ አደራጅተው እየመሩ ስላገሩ የሚከላከለውን አርበኛ ይወጉ እንደነበረው ያን ጊዜም የግራኝ የጦር አለቆች ይኸንኑ ሠርተዋል ፡፡ ተክለ ጊዮርጊስ በአንዱ በር ተዋግቶ ወደሌላው በር ለመሸሽ ሲሄድ ድንገት ከሻምሱ ጋር ተገናኝቶ ተዋግቶ የሞተው ይህ የእስላም የጦር አለቃ በውስጥ አወቅ ያገር ተወላጅ እየተመራ አልፎ ሁለተኛውን በር ይዞ ስለተጠባበቀው ነው ፡፡

ከዚሁ ከተክለ ጊዮርጊስ ውጊያና ሞት በኋላ ዓረብ ፋቂህ ስለራስ ነቢያትና ስለፍቅረ ኢየሱስ ውጊያ እንደዚህ ሲል ያነሣል ፡፡ «ይማም ከቤተ አምሐራ ወደ ደብረ ብርሃን የመጣ ጊዜ የሀበሻው ንጉሥ ወናግ ሰገድ ሂፊን ወደሚባል ወደ ባሕር ዳባ ሄደ ፡፡ ባሕር ዳባም ጥሩ የሚጣፍጥ የባሕር ሐይቅ ነው . . . . . ንጉሡ በአበሾቹና በክርስቲያኖቹ ዘንድ የተከበረውን ጕበዙን ራስ ባንያትን እስላሞቹ ሁሉ ያሉት ደብረ ብርሃን ነው ፤ አውራይ አቡን በይፋት ወደኋላ ቀርቷልና ሄደህ እጁን ይዘህ አምጣው» ብለው እንደላኩትና ሲልኩትም ግራኝ ቀደም አድርጎ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 354 - 357

ስዚሁ ለአውራይ አቡን ብዙ የጦር እርዳታ መላኩን አለማወቃቸውን ይገልጻል (1) ።

ከዚሁ አያይዞ « ራስ ባንያት በክርስቲያኖቹ ዘንድ የከበረ ነው» እያለ ስሙንም ነቢያት በማለት ፈንታ በስሕተት ባንያት ቢለውም የተከበረ ነው ሲል ያነሣው እውነቱ ነው ። በኛም ዘንድ የግዕዙ ጽሑፍ ራስ ወሰን ሰገድንና ራስ እስላም ሰገድን እያቀናጀ የግራና የቀኝ ቢትወደድ እያለ እንደሚያወሳቸው ራስ ነቢያትንና ከዚህ በፊት ስሙን የጠራነውን ቢትወደድ ሠርጼን ግራና ቀኝ እያደረገ ይጠራቸዋልና የራስ ነቢያት ደረጃ ከነዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ነው (2) ።

እንደዚሁም አልቫሬጽ በመጽሐፉ «ወደቤተ መንግሥቱ በደረስን ጊዜ ከባል ደረባችን አንዱ ግራጌታ የሚያሰኝ ማዕርግ ያለው ራስ ነቢያት ነው ፤ እርሱም በፊት ባሕር ነጋሽነት ቀጥሎ ቢትወደድነት ተሾሞ ነበር» ሲል ገልጿል (3) ።

ራስ ነቢያት አንባቢ እንደሚያስታውሰው ከዚህ በፊት በደዋሮ ተዋግቷል ። ንጉሡም ዋስል የነበሩ ጊዜ በመንዝ በኩል ያለውን ሦስተኛውን በር ይዞ ግራኝን እንዲከላከል የተመደበው እርሱ እንደነበረ እናስታውሳለን ።

አሁን ንጉሡ ወደ ይፋት ከአውራይ አቡን ጋር እንዲዋጋ ሲልኩት ለአውራይ አቡን የተላከውን የጦር እርዳታ ሳይገነዘቡ «እጁን ይዘህ አምጣልኝ» እንዳሉት ጸሐፊው ይገልጻል ፤ ጸሐፊውም ባሁኑ ድል በሆኑበትና የግራኝ ጦር ባየለበት ሰዓት ምንም እንኳ በግሼን እምባ እነቢትወደድ ሠርጼ ያገኙት ድል የተስፋ ጮራ ቢፈነጥቅ «እጁን ይዘህ አምጣልኝ» የሚል የኩራት ትእዛዝ የሚሰጡ አይመስልም ። ጸሐፊውም ከንጉሡ አንደበት መውጣቱን ወሬ ሰምቶ ነው እንጂ በአጠገባቸው ሆኖ እንዳልሰማ የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ዓረብ ፋቂህ የአሁኑን የራስ ነቢያትንና የፍቅረ ኢየሱስን ጦርነት እንደዚህ ብሎ ይወስናል ። «ራስ ባንያትና አዝማች ፍቅረ ኢየሱስ ወታደሮቻቸውን ይዘው መጥተው እስላሞቹ ወደ አሉበት ወደ ቂሳያህ (ይፋት ውስጥ) መጡ . . . . . . እስላሞቹም በሩቅ ባዩዋቸው ጊዜ ለጦርነት ተሰለፉ . . . . . . . ሁለቱ ወገኖች ከተቀራረቡ በኋላ ከእስላሞቹ ውስጥ ሳብር አድ. ዲን. የሚባለው ፈረሰኛ ቀድሞ ጦርነቱን ሲከፍተው እስላሞቹም ተከትለውት ገቡና ወታደር ለወታደር ተደበላልቆ ይዋጋ ዠመር ። በዚያን ጊዜ አባስ (4) ወደራስ ባንያት ገሥግሶ ሄደና በሰይፍ ቢመታው የራሱ ቆብ ሲሶው ከፈረሱ ዡሮ ጋር ተቆርጦ ከመሬት ወደቀ ። በዚያን ጊዜ ባንያት ፊቱን መልሶ ሸሸ ። ክርስቲያኖቹም ተዘበራርቀው ሽሽት ዠመሩ ። እስላሞቹም ከእኩለ ቀን ዠምረው እስከ ማታ ድረስ እየተከታተሉ ሲፈጁዋቸው ዋሉ ። ከዚያ ወደ ማታ የማረኩትን ፈረስና በቅሎ ይዘው ወደ ሠፈር ተመ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 357 - 358

(2) Liber Axum-Conti-Rossini ገጽ 31 - 33

(3) አልቫሬጽ ምዕ. 180 ገጽ 276

(4) የግራኝ የወንድም ልጅ ዓረብ ፋቂህ 317

ለሱና ያገኙትን ድል ለይማም ላኩበት ። መላከተኛውም ደብረ ብርሃን ደርሶ በነገ ረው ጊዜ ይማም አህመድ ታላቅ ደስታ ተሰማው» (1) ።

የሆነ ሆኖ አሁንም ራስ ነቢያት ከዚህ ጦርነት ተመልሶ ወደ ንጉሡ መሄዱንና እንደገና በወረባ ያኪም ከሚባል የጦር አለቃ ጋር መዋጋቱን ወደፊት እንመለከታ ለን ።

## ምዕራፍ ፳፱
## የተጉለት ፤ የይፋት ፤ የደዋሮና የወጅ ፤ የዝቋላ ዙሪያ አገሮች ለግራኝ እየገቡ መስ ለም (፲፭፻፳፱ - ፴፫ ዓ. ም.)

ግራኝ አህመድ ከቤተ አምሐራ ተመልሶ ከወዚር አዶሌ ጋር በደብረ ብርሃን ከተገ ናኙና በተጉለት ዝግናው ተክለ ጊዮርጊስ ከሞተ በይፋትም ራስ ነቢያትና ፍቅረ ኢየሱስ ተሸንፈው ከሸሹ በኋላ ለተጉለትና ለይፋቱ ግዛት የወንድሙን ልጅ አባስ ንና አውራይ አቡንን ትቶ እርሱ ራሱ ከዚህ በፊት አጉረፍርፎ ያለፈውን የደዋሮን ግዛት በትክክል እያጣራ ለማሳመን ጉዞ ሲዠምር አውራይ አቡንና አባስ እኛ እዚህ እክርስቲያን አገር ቀርተን አንተ ወደ ደዋሮ ስትዘምት በመካከሉ ክረምት ገብቶ አዋሽ ቢሞላ ካንተ ጋር ተቋርጠን እንቀርና በዚያን ጊዜ ንጉሡ በመካከል መጥቶ ቢወጋን እንቸገራለን ቢሉት ምንም ቢሆን አሁን ሕዝቡን አስገብረን ግብ ሩን ከበላችሁ በኋላ እንደዚሁ ትታችሁት ከኔ ጋር ልትሄዱ አይገባም ብሎ የአቡ በከርን ጦር ጨምሮላቸው እርሱ ወደደዋሮ ሲጓዝ አውራይ አቡን አባስንና አቡበከ ርን ትቶ እርሱ ወደ ግራኝ መጥቶ አብሮ ወደ ደዋሮ ጉዞ ተዠመረ ።

በዚሁ ጊዜ የግራኝ አንድ ክፍል ጦር በፈራቃሃም ዲን እየተመራ ሲጓዝ በሌላ በኩል ደግሞ በዝቋላ አቅራቢያ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ጦርነት ሲዠመር ራሱን መግታት የማይችለው በሻራህ የሚባለው የፈራቃሃም ዲንን ምክር ጥሶ ሲያልፍ በቀስት አመታት ስመ ጥር የሆኑት የማያ ሰዎች ጦርነት ገጥመውት ሲዋጉ አንዱ የማያ ጦረኛ አነጣጥሮ በቀስት የበሻራህን ፊት መትቶ ገደለው ።

ነገር ግን በሻራህ ከሞተ በኋላ መዠመሪያ ገራድ ሻሙንና ገራድ ኡስማን ቀጥሎ ራሱ ፈራቃሃም ዲን ወደ ማያዎቹ ሄደው ተዋግተው አሸነፉዋቸው ። ከዚህ በኋላ እስላሞቹ በያለበት እየተበታተኑ የማያን ሕዝብ ሲፈጁ ሰንብተው የቀረውን በማሳመን እየሰበሰቡ አሰለሙት ፤ አለቃቸው ዘርጂር (ዘርጊ ?) ብቻ እኔ የምሰል መው ከይማም አህመድ ፊት ነው እንጂ እሹማምንት ፊት መስለም ውርደቴ ነው ስላለ ውሎ አድሮ እንደተመኘው ግራኝ አህመድ (ይማም) ወጅ የነበረ ጊዜ ቀርቦ ሰለመ ።

የወጅ ሹም እስላም ደሀር ፤ የዝቋላ ዙሪያ ሹም ተስፉ ፤ ዮናዳብ የሚባል የን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 357 - 359



በዚህ ሰነድ የእስላም ደሀር አባት ቍም ደሀር ባዬ ልብነ ድንግል አያት ባዬ በእደ ማርያም ዘመን የወጌ ቃጽነት (የወጀ ሹመት) ይዞ እንደነበረ ከሌሎች ሹማምንት ጋር ተጠቅሶ ይታያል ። ገዞ ብሎ በ፳ኛው ዓምድ ባዬ ልብነ ድንግል ዘመን ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስ ቀጥሎ ከጽራግ ማሠሬ እሥራት በፊት ስሙ ተጠቅሶ ይገኛል ። ስለዚህ የወጅ ግዛት ለእስላም ደሀር ካባት የወረደ ነው ማለት ነው ። ሰነዱ በፎቶ የተነሣው በብር ብር ማርያም (ገሙጐፋ) ከሚገኝ ካንድ የብራና ወንጌል ዳር ነው ፤ ያገኙትና ያነሡት ማዳም ስፒንሰር ናቸው ።

ጉሡ እማች ባንድነት ሆነው ለመከላከል ካሰቡ በኋላ የዝቋላው ተስፋ መከላከሉ ምንም ረብ እንደማይሰጠው ስለተገነዘበው ከነጭፍራው ወደግራኝ ገብቶ ሰለመ ። ዮናዳብ በበኩሉ ለግራኝ ገብቶ መስለሙ የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ስለሆነበት ከእስላም ደሀር ጋር ወደ ጉራጌ አገር ከሄዱ በኋላ ከዚያ መሄድ ካልፈለገው ከእስላም ደሀር ተለይቶ ሚስቱንና ጓዙን ይዞ መቶ ሃምሳ ፈረሰኛ እንዳስከተለ ንጉሡን ፍለጋ ወደ እንጐት ሄደ ። እስላም ደሀር ደግሞ ከጓደኞቹ ከዮናዳብና ከተስፋ የተለየ ሌላ መካከለኛ የመውጫ ዘዴ በመፈለግ "ሃይማኖቴን መለወጤ በንጉሡ ዘንድ የተሰማ እንደሆነ ታላቅ ውርደቴ ስለሆነ እየገበርሁህ ሃይማኖቴን ይገፍ ልቀመጥ አገሬም አይዘረፍ ቤተ ክርስቲያኔም አይቃጠል" የሚል የልመና ቃል ጨምሮ መላኩን ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል በራሱ አነጋገር ባጭሩ ያብራራል ።

«አገሩ እንዳይዘረፍበት ፥ አብያተ ክርስቲያኑ እንዳይቃጠሉበት ስለፈራ እስላም ደሀር ልጁን ከ፴ ፈረሰኞች ጋር አስቦ የሚባል ሹም ጨምሮ ወደ ይማም ላከ ። መላክተኞቹም በደረሱ ጊዜ ዋናው ሹም (እስላም ደሀር) ለምን አልመጣም ብሎ ጠየቃቸው ። እርሱ ወዳንተ የመጣ እንደሆነ በንጉሡ ዘንድ ውርደት ይሆንበታል ። ነገር ግን ስለርሱ ይኸው ልጁን ልኳል ብትፈልግም አስልመው ብሎ አባትየው ፈቅዷል አባቱም ግብር ይገብራል ብሎ አስቦ መልስ ሰጠ ።

በዚህ ጊዜ ይማም ከጓደኞቹ ጋር ተማከረ ጓደኞቹ አባትዬውን አንፈልገውም ሃይማኖቱን ይዞ ይቀመጥ ልጁ ግን ይስለምና ከኛ ጋር ይሁን ስለአሉ ይማም አሳባቸውን ተቀበለ ። ስለዚህ ክርስቲያኖቹን ሰበሰቡና "እግዚአብሔር አምላክ ነው መሐመድም ሐዋርያው (መላክተኛው) መሆኑን እንመሰክራለን በሉ" አሉዋቸው ። አስቦ ይኸንኑ ቃል መልሶ ተናገረና ሰለመ ። የእስላም ደሀር ልጅ ደግሞ ልጅ ልታደርገኝ ማልልኝና ነው የምሰልመው ብሎ እምቢ አለ ። ይማም ሳቀና ግዴለህም የፈለግኸውን ሁሉ ታገኛለህ ብቻ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ እግዚአብሔር የለም ሐዋርያው መሐመድ ነው ለርሱም እግዚአብሔር በረከትንና ደህንነትን ይስጠው በልና ስለም አለው ልጁም እሺ ብሎ ይኸንኑ ቃል ተናግሮ ሰለመ ፤ ከርሱም ጋር የመጡት ፴ ፈረሰኞች ይኸንኑ ፈጽመው ሰለሙ ። ይማም ልብስ ሰጣቸው አይዟችሁ አትፍሩ ብሎ አጽናናቸውና ከርሱ ጋር አስቀመጣቸው ። ከዚያ ቀጥሎ ተስፋም የዝቋላው ገዥ በፋራቃሃም ዲን እጅ ስልሚያለሁና አገሬ አይዘረፍ ወታደሬን ይዠ ወዳንተ እመጣለሁና ሰው ላክልኝ ብሎ ወደ ይማም ላከ ይማምም ያኪምን ልኮለት ከርሱ ጋር መጥቶ ከይማም ተገናኘና እንግዲህ በያኪም ውስጥ ሆነህ አገልግል . . . . . . አለው ።

ከዚያ በኋላ ፋራቃሃም ዲን በርሱ እጅ የሰለሙ የ፷ አገሮች ሕዝብ ከፈረሰኛው ከየአለቃው ጋር ሆኖ ወደ ይማም መጣ ። ይማም ብዛታቸውን አይቶ አምላኩን አመሰገነ . . . . . አብድ ኢን ናስር ጋንዝ አጠገብ ያሉትን የከምባታ ሰዎች ሊወጋ ሄደ ከምባቶችም ከጋፋት ሰዎች ጋር ተደባልቀው ውጊያ ዠምረው ነበር በኋላ ግን ተሸንፈው ገበሩ ። ከዚያ ወደ ሀድያ መጣና ተዋጋ ነገር ግን ከእስላሞቹ ውስጥ ሁለት የታወቁ ሰዎች ሲሞቱ የቀሩት ሸሹ አብድ ኢን ናስርም ከ፲፪ ጓደኞቹ

ISIC

ጋር ጠንክሮ ሲዋጋ የሸሹት ተመለሱ ከዚያ በኋላ ክርስቲያኖቹ ሸሹ የቀሩትም በጦርነቱ ላይ ሞቱ አብድ ኢን ናስርም በዚሁ አገር ላይ ተቀመጠ ። በዚሁ ጊዜ ይማም አህመድ የረማዳንን ጾም በወጅ ጾሞ በጉራጌ አገር ጾሙን ፈታ» (1) ።

ይህ በአለፈው የተመለከትነው ግራኝ አህመድ ንጉሡን አባርሮ ለመያዝ ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ ሳይሆንለት በዚያ አውራጃ የሚገኙትን ታላቅ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት አቃጥሎ ከተመለሰ በኋላ የሠራው ነው ። ንጉሡም በሽምብራ ኩሬ ላይ በ፲፰፻፳፩ ዓ. ም. በመጋቢት ፳፩ ቀን ተዋግተው ተሸንፈው ወደቤተ አምሐራ ከዚያም ወደ በጌምድር ከገቡ ወዲህ የቀድሞዎቹ መኳንንት እነራስ እስላም ሰገድ እነራስ ወሰን ሰገድ ከሞቱ አሁንም በቅርብ መጥቶ የነበረው ራስ ነቢያት ተሸንፎ ከተመለሰ በኋላ ለግራኝ በዚሁ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የኢትዮጵያ ክፍል ከባድና አስጊ ጦር እንዳልነበረበት እንመለከታለን ።

ስለዚህ ግራኝና የጦር አለቆቹ ቀድሞ ራስ ደገልሃንን ካሸነፋበት ከ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ ንጉሡን እስከአሸነፋበት እስከ ፲፰፻፳፩ ዓ. ም. ድረስ እየተዋጉ በወረራ ያለፉበትንና ያላለፉበትን አውራጃና ወረዳ በአሁኑ ሰዓት ግራኝ ብዙ የወርቅ ሀብትና የሀር ልብስ ይዞ ከቤተ አምሐራ ከተመለሰና ከእንደራሴው ከወዚር አዶሌ ጋር በታላቅ ሰልፍና በደስታ ደብረ ብርሃን ከተገናኙ በኋላ እርሱና የጦር አለቆቹ ባሁኑ ጊዜ (፲፰፻፳፰ ዓ.ም.) በረጋ መንፈስ በተረጋገጠ ልብ በይፋት በተጉለት በፈጠጋር (ቡልጋና ም፲፱፻ር) በጉራጌ ፣ በዝቋላ ዙሪያ ፣ በከምባታ ፣ በሐድያ ፣ በጋንዝ (ግንጭ ?) በጉራጌ እንደልባቸው እየተዘዋወሩ ሲዋጉ ፣ ሲዘርፉ እንደልባቸው ሲያዙ ፣ ሕዝቡን ሲያሰልሙ ፣ ሲያስገብሩ እንመለከታለን ።

ከታላላቆቹ መኳንንት ከነራስ ወሰን ሰገድ ውድቀት በኋላ ከአይፈርስና ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ ንጉሡም ወደ ቤጌምድር ከዘለቁ በኋላ በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ሁሉ የደቡብ አገሮች በበላይ አለሁላችሁ የሚል ሁሉን ባንድነት ሰብስቦ የሚያዋጋ የበላይ መሪና አለቃ እንዳላገኙ ይታያል ። በጀግንነት ስመ ጥር የነበረው ራስ ነቢያትም ባለፈው እንደተመለከተው ከንጉሡ ታዞ በመንዝ አልፎ ወደ ይፋት መጥቶ ከአባስ ጋር ብቻ ለብቻ ገጥመው ዓረብ ፋቂህ የሚለው እውነት እንደሆነ የፈረሱ ዠሮና የራሱ ቆብ በሰይፍ ተቆርጦ ከወደቀበት ወዲህ ነፍሱን ለማዳን ሸሽቶ ወደመጣበት ተመልሷል ። የተመለሰውም ንጉሡ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ወደ ቤገምድር ወይም ወደ ጐጃም መሆን አለበት ። እንደዚሁም ሳፉ (ሳፍ ሰገድ) የሚባለው የሟቹ የራስ ወሰን ሰገድ ልጅ በደዋሮና በሌላውም ክፍል ሲከላከል ከቆየ በኋላ ተስፋ በመቁረጥ ከጓደኞቹ ከአምሃና ከፋኑኤል ተለይቶ ንጉሡ ወደሚገኙበት ወደ አንጐት (ላስታ ጕን) መሄዱ ተመልክቷል (2) ።

(1) ዓረብ ፊቂህ ገጽ 359 - 366
(2) " " " 367 - 370



ዓፄ ልብነ ድንግል ለራስ ወሰን ሰገድ መታሰቢያ (ተዝካር ማውጫ ?) እንዲሆነው በተለይ ለልጁ ለሳባ ሰገድ ጉልት የሰጡበት ታሪካዊ ሰነድ ፡ ዝርዝሩን በግልባጩ ተመልከት ።

በእስላሞቹ በተወረረው አገር የግራኝ ሥልጣን በተዘረጋበት ጊዜ በሌላው ባልተያዘው አገር ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ሹም ሽር እንደሚያደርጉበት ሳገለገለም ጉልት እንደሚተክሉ ይህ ሰነድ ያስረዳል ። ከሰነዱ ላይ እንደሚታየው በቀኝ ዓረብኛው ዓፄ ዳዊት (ሺ.፫፻፸፬ - ሺ.፬፻፮ ዓ. ም.) ድል መንግሣ ላሠራችው ለቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን የጸሃንና የቅውይስን . . መሬት የጐለቱበት ፤ በግራ በግብጢ ቋንቋ በኋሁ ባፄ ዳዊት ዘመን በርተሎሜዎስ የሚባሉት ጳጳስ ቅዱሱን ቦታ (ላሊበላን) ለመጐብኘታቸው የተጻፈ ሲሆን በግርጌ ያለው ግዕዛዊው ጽሑፍ ዓፄ ልብነ ድንግል የዝብጋዝን ምድር ለሳፍ ሰገድ ለራሱና ከግራኝ ጋር ሲዋጋ ለሞተው ላባቱ ለራስ ወሰን ሰገድ ተዝካር ማውጫ (ወይም መታሰቢያ) በጉልትነት የተከሉበት ነው ። በዚሁ ሰነድ ትክሉ እንዳይፈርስ ያወገዙበትና በአተካከሉ እንደምስክር የቆጠሩዋቸው የባለሥልጣኖች ስም በማይነበብ አኳኋን ይገኛል ። ተተካዩ ሳፍ ሰገድ ባጭሩ ሳፉ ይባላል ። አባቱ ራስ ወሰን ሰገድ በሺ.፬፻፳፫ ዓ.ም. ከግራኝ ጦር ጋር ሲዋጋ ከሞተ ወዲህ እርሱ ከጓደኞቹ ከፋኑኤልና ከአምሐ ጋር በደዋሮ ከተከላከለ በኋላ በመጨረሻ በዚህ ክፍል መቆየት ስላልቻለ ከጓደኞቹ ተለይቶ ንጉሡ ወደ ሄዱበት ወደ አንጐት (ላስታ) ሂዶ ተገናኝቷል ። (ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 367 - 370) ። ጉልቱን ያገኘው በዚያን ጊዜ ፤ መሬቱም የሚገኘው በዚያ አካባቢ ይመስላል ። ሰነዱ የተገኘው ከቅዱስ ላሊበላ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ላይ ነው ። በዘመን ብዛት ጽሑፉ የተድበዘበዘ ቢሆንም ቃሉ በግዕዝ ከወደ መዠመሪያው ላይ «በአኰቴተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አኰለትኩ አነ ወናግ ሰገድ ወስመ መንግሥትየ ልብነ ድንግል ለምድረ ዝብጋዝ ከመ ይኩኖ ርስተ ለሳፍ ሰገድ ወተዝካረ አቡሁ ወሰን ሰገድ በእንተ (ከዊነ ሞቱ ?) ከመ ቱዎድሮስ ወገላውዴዎስ (ሰማዕታት) በእደ ግራኝ አላዊ ሃይማኖት . . . .» ሲል ይነበባል ።

(LALIBELA - A.A. MONTI DELLA CORTE. ገጽ 136-140)

## ምዕራፍ ፳

### የማያ ሕዝብ ከነመሪው ወደ ግራኝ መግባትና መስለም ።

የማያን ሕዝብ ዓረብ ፋቂህ ብዙ ጊዜ በጽሑፉ ኤልማያ (ማያዎቹ) ይላቸዋል ። እነ ርሱም የግራኝ ጦርነት ከተጀመረ እንሥቶ በቀስት አመታት ጦሩን ምን ያህል እን ደጐዱበት እንብበናል ። ለማስታወስ ያህል በባደቂ ጦርነት ሰውነት የሚያቃጥል መርዝ በተቀባው ቀስታቸው ሲዋጉ እስላሞቹ እንደገና አግኝተው እንዳይጠቃሙ በት በግራኝ ትእዛዝ ተሰብስቦ ሳለ ወደ ማታ እንጨት በማይገኝበት ቦታ ኩበት አርደው ማብሰያ ባጡ ጊዜ በርሱ አብስለው እንደበሉ ፤ ፫ሺ የሚሆኑ የማያ ጦረ ኞች ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት በፊት ንጉሡን ለመርዳት ሲመጡ በድንገት የወገና ቸው የክርስቲያን ጦር መሸሿቸው ከግራኝ ጦር ሠፈር ገብተው በእስላሞቹ እጅ እንደተፈጁ አለቅዬው ተይዞ ከግራኝ ፊት በቀረበ ጊዜ "በ፱፻ ወቄት እበጃለሁና ከፍዬ ልለቀቅ" ቢል ግራኝ "ያንተ ወርቅ አያስፈልገንምና ይኸን ውሻ ግደሉት" ብሎ እንዳስገደለው እንብበናል ።

በዝቋላ አካባቢ ግራኝ ራሱ ወይም ጦሩ በተላለፈ ቍጥር ፊት ለፊትም በደፈ ጣም በቀስት ውርወራ ብዙ እንደፈጁበትና እንዳስጨነቁት በመጨረሻ በዚሁ ዓመት ፈራቃሃም ዲን አገራቸውን ተሾሞ ሳለ በርሱ ጦር ውስጥ የዘመተው በሻራህ የአለቃውን የፈራቃሃም ዲንን ምክር እምቢ ብሎ ሄዶ ከማያዎቹ ጋር እየፎከረ ሲዋጋ አንዱ የማያ ጦረኛ አነጣጥሮ በተመረዘ ቀስት ፊቱን መትቶ ገድሎታል ። ከበሻራህ ሞት በኋላ ዋናው መሪ ፈራቃሃም ዲን ቍጥሩ የበረከተ ጦር ይዞ ሄዶ በመ ግሪያና በጦር ሠራዊት ብዛት ከደመሰሳቸው በኋላ እነዞ ባለፈው እንደተመለከት ነው በጅምላ እየገቡ ከነአለቃቸው ሰልመዋል ።

የአለቃቸውን ስም ዓረብ ፋቂህ ባንድ ቦታ ላይ ዘርጊሀ ይልና እርሱም "ከይ ማም አህመድ ፊት እንጂ ከሹም ፊት አልሰልምም" ብሎ በኋላ መስለሙን ከገ ለጠ በኋላ በሌላ ላይ ደግሞ ተስፋ የሚባለውን የዝቋላ ሹም ስለሚያደርገው ዘርጊ የተባለው ያው ተስፋ ሳይሆን አይቀርም ወይም ዘርጊ የማያዎቹ ባላባት ሆኖ ተስፋ ደግሞ በበላይ ከንጉሠ ነገሥቱ የተሾመ የጦር መኰንንና ገዥ እንደሆነ በትክክል አይታወቅም ።

የሆነ ሆኖ የማያ ሕዝቦች ባሁኑ በግራኝ አህመድ ጦርነት ጊዜ መኖሪያ ሥፍራ ቸውን በዝቋላ አቅራቢያ ሲያደርገው ቀደም ብሎ ባለው በነዓዴ እስክንድር ዘመን በደንከል ወይም በዛሬው አሰብ በተለይ ጨው በሚወጣበት አካባቢ ያደርጋቸ ዋል ። ዓፄ እስክንድር (፲፬፻፹፰ - ፲፬፻ ፺፰ ዓ. ም.) ከአዳሉ ንጉሥ ከሻምስ አድ ዲን ጋር በተዋጋበት ጊዜ ዘሥሉስ የሚባለው የጦር አለቃው እስክንድርን አጋልጦ እን ደተመለሰ በኋላም ከማያ (እርኖ) ተወላጆች ጋር ዶልቶ እንዳስገደለው እስክንድር ንም በቀስት በትር የገደሉት በአፋርና በትግሬ መካከል የሚገኙ ከአሰብ ጨው እያ መላለሱ የሚነግዱ መሆናቸውን ጀምስ ብሩስ ያረጋግጣል (1) ።

(1) የአበሻና የኑብያ ጉዞ - ፪ኛ ቮሊዩም የካስትራ ትርጉም ገጽ 125

ISIC

ያዔ እስክንድር ዜና መዋዕልም ዓፄ እስክንድር በቤተ መንግሥቱ ሳለ ወዳጅ ህን ተክላይን ማያ የሚባሉት የአርኖ (አረሆ ?) ሰዎች ገደሉት ማለትን ስለሰማ ከመሸ በኋላ ተነሥቶ ወደ እነሱ ሲሄድ በጭለማ ንጉሥ መሆኑን ሳያውቁ ነድፈው እንደገደሉት ይገልጻል (1) ።

አሁንም አርኖ የሚባሉ ጨው በሚወጣበት በአሰብ እንደሚኖሩ የታወቀ ሲሆን እነዚህ ማያዎቹ በቀን ብዛት ከዚሁ ቀበሌ ወደ ደቡቡ ክፍል ወደለምለሙ አገር ወደ ዝቋላ መጥተው ክርስትናን ተቀብለው ሲኖሩ አሁን በግራኝ ጊዜ ደግሞ ከክርስቲያኑ ወገናቸው ጋር ተዋግተው ከተሸነፉና ለግራኝ ከገቡ በኋላ ለርሱ መሣሪያ ሆነው ያልገበረውን ለመውጋት ውዴታም ግዴታም ሆኖባቸዋል ።

እነዚህ በቀስት አመታት ስመ ጥር የሆኑት የማያ ተወላጆች ግራኝ ከሞተ በኋላ በጋሎች ወረራ ጊዜ ከጋሎች ጋር ሲዋጉ መሸነፋቸውን የጋሎችን ታሪክ የጻፉት አባ ባሕርይ ዜና ጋላ በሚባለው በግዕዝኛ መጽሐፋቸው ላይ እንደዚህ ሲሉ ጠቅሰውት ይገኛል ። “. . . . . . ከስምንተኛው ዓመት በኋላ የኪሎሌ ልጅ ቢርመጅንት ተሾመ ። እርሱም ደዋሮን ያጠፋው ነው ። ይኸው ቢርመጅ የቦረኑ በበሬ ቆዳ በሰው ቁመት ልክ ጋሻ አሠርቶ ቀስተኞች ከሆኑት ከማያ ሰዎች ተዋግቶ አሸነፋቸው ። ያሸነፈበት ምክንያትም በሙሉ ሰውነቱን በደረቀ የቆዳ ጋሻ ሸፍኖት ስለነበረ ማያዎቹ በቀስት የሚመቱበት ቦታ ስላጡ ነው” (2) ።

በጐንደር ዘመነ መንግሥት ማያዎች ፩ ጊዜ ከጋሎች ሌላ ጊዜ ከጋፋቶች ጋር እየተደረቡ ሲሸፍቱም ሲታመኑም ቆይተዋል ። የሱስንዮስ ዜና መዋዕል በብዙ ቦታ ላይ በዚሁ ምክንያት ስማቸውን አልፎ አልፎ ይጠቅሰዋል ። በዓፄ ሱስንዮስ ጊዜ ሹማቸው ቦሻሳ ይባላል (3) ። የነዚህም የሰዎች ኑሮ በየሥፍራው ሲነበብ ባንድ አውራጃ ትክለኛ ሳይሆኑ በብዛት ከብት እያረቡ ካገር ወዳገር እየተዘዋወሩ በወዶ ዘማችነት ጭምር የሚኖሩ ይመስላል ።

ግራኝ አህመድ ከነጦሩ ከገበርጌ (ወጅ) ወደነርሱ አገር (ወደ ዝቋላ አካባቢ) የመጣ ጊዜ «የማያዎች አገራቸው በጫካ የተሸፈነ መንገዱ ጠባብ ነው ። ከዚህም ጋር ከቀንድ ከብት በቀር ምንም ስለሌላቸው በተመረዘ ቀስታቸው እየነደፉ እንዳይጐዱን ከብታቸውን አትንኩ» ያለው ቤትና ንብረት የሌላቸው ያስመስለዋል (4) ።

(1) ወእምዝ በአሐቲ ዕለት እንዘ ሀሎ ውስተ ጽርሑ ነገርዎ እንዘ ይብሉ ቀተልዎ ለተክላይ ገብርከ ዘታፈቅሮ ሰብአ አርኖ ወበእንተዝ ተንሥአ በጊዜ ምሴት ወበጽሐ ኀቤሆሙ . . . . . ወኢያእመሩ ከመ ንጉሥ ውእቱ ወነደፍዎ እሉ ሰብአ አርኖ ዘይሰመዩ ማይ (ማያ) . . . . . . ፔሩሾ ያሳተመው የእስክንድር ዜና መዋ ፡ ገጽ 343 ።

(2) ወእምድኅረ ፰ቱ ዓመት ተሠይመ ቢርመጅ ወልደ ኪሎሌ ዘአጥፍአ ለደዋሮ ። ወዝንቱ ቢርመጅ ዘቦረን ገብረ ወልታ ዘአንዳ ላህም መጠነ ቆሙ ወፀብዖሙ ለማያ ሰብአ ቀስት ወሞዖሙ ሶበ ኀጥኡ ዘይነድፍዎ እስመ ተወልተወ እነዳ ላህም ይቡስ . . . . .” ዜና ጋላ ጉይዲ ያሳተመው (LOUVAIN) ገጽ 226 - 227

(3) ፔሬይራ ያሳተመው የሱስንዮስ ዜና መዋዕል ገጽ 142 . 147 . 232. 288

(4) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 212 ።

ከመጀመሪያው ላይ በደንከል በዋግ ከዚያ ወደ ዝቋላ ቀጥሎ ወደ ዳሞት ወደጋፋት እየተበተኑም እየተሰበሰቡም ኖረዋል ። በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በሐረርና በድሬ ዳዋ መካከል ከአቡበከር በታች ያለው የአማሬሳ ወንዝ ወደሚደባለቅበት ወደ ጉበሌ ወንዝ የሚገባ የማያ ወንዝ የሚባል ስለ አለ በዚያም አቅራቢያ ሠፍረው ነበር ለማለት ይቻላል ።

በዛሬ ጊዜ ማያ እየተባለ የሚጠራ ሕዝብ በአሞ ወንዝ አካባቢ በሐድያ ባደጎ በተባለው ጐሣ ውስጥ በምዕራብ በኩል መገኘታቸውን በሐድያ ቋንቋ ማያ ማለት "ምን ብሎ ወይም ምን አለ" ማለት መሆኑን አቶ ኃይሌ ቡባም ያረጋግጣሉ ።

## ምዕራፍ ፸፩
## የሐድያው ባላባት ለግራኝ አህመድ መግባትና መጋባት

በዚህ በግራኝ ጦርነት ጊዜ በደቡቡ ክፍል ከክርስቲያኑ እስላሙ የበዛበት ወረዳ እንደደዋሮ እንደ ሐድያ ያለው ከእስላሙ ክርስቲያኑ እንደሚበረክትበት እንደ ሸዋ እንደ ይፋት እንደወጅ ፣ እንደ ጋንዝ አበክሮ የግራኝን ወረራ አልተቋቋመም ። ምክንያቱም ለማንም የተሠወረ አይደለም ። ስለደዋሮው ሕዝብ አገባበር አንድ የልብነ ድንግልን ታሪክ በግዕዝኛ የጻፈው እንደዚህ ሲል አብራርቶታል «ግራኝ ደዋሮን የወረረ ጊዜ ከሕዝቡ አጋማሹ የሰይፉን በትር በመፍራት የቀረውም አብዛኛው ሕዝብ ሃይማኖቱ ከግራኝ ሃይማኖት ጋር ስምም ስለሆነ ሁሉም ተገዛለት» (1) ። ብዙ ጊዜ በደዋሮ ጦርነት መደረጉን ዓረብ ፋቂህና ታሪክ ነገሥቱ ቢያወሱም አብዛኛ ጊዜ የተዋጋው ከወዲህ ታዞ የሄደ ወይም እዚያው በአገዛዝ የተቀመጠ የክርስቲያን ጦር ነው ።

በዚህ ሁሉ የተነሣ የሐድያ ሕዝብ ከነዋሪው ሕዝብ አብዛኛው ከነባላባቱ እስላም ስለሆነ የግራኝን ወረራ ጐረቤቱ የማያ ሕዝብ የቀረውም ያማራና የትግሬ ተወላጅ ባደረገው ተጋድሎ ዓይነት አልተቋቋመም ።

የዚህን ዘመን የኢትዮጵያን ካርታ ካዘጋጁት ውስጥ እነክራፕስ እነቦረሊ (Kraps, Borelli) የሐድያ ወረዳ የሚገኝበትን ሥፍራ በምዕራብ ከጃንጀሮ በሰሜን ከጉራጌ በደቡብ ከከምባታ በምሥራቅ ከዟይ ደሴት እንደሚዋሰን ያመለከቱትን ዛሬም እነዶክተር ቤንደር (M.L. Bender) ነዋሪ የኢትዮጵያ ቋንቋ (Language Survey of Ethiopia) ብለው ባወጡት ካርታ ላይ ያመለከቱት ከነዚሁ የቀድሞ ካርታ ሠሪዎች ምንም ያህል አልራቁም ። እርሳቸውም በካርታ ላይ በዝርዝር ሲያመለክቱ ከሐድያ ሰሜን እንደጋኝ ፣ እንቆረርና ጉመር (ጉራጌ) ከምሥራቅ በኩል

(1) ወሰበ በጽሐ ደዋሮ ገሪሩ ሎቱ ቱሉሙ ሰብአ ሀገር መንፈቆሙ በፍርሃተ ሰይፉ ፡ ወመንፈቆሙ በእፍቅሮተ ሃይማኖቱ ፡ እስመ መብዝኅቶሙ ለሰብአ ደዋሮ ዝዉጋን ምስሌሁ በሃይማኖት . . . .
የዓፄ ልብነ ድንግል ታሪክ ኮ. ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 12 ።

ISIC

ማረቆ ከማረቆ ወደ ደቡብ አላባ በአላባና በሐድያ መካከል ከምባታ ከሐድያና ከከምባታ በስተደቡብ ወላሞና ኩሎ ከሐድያ ምሥራቅ ጃንጀሮና የቦሻ ጐሣ እንደሚገኝ አድርገውታል ።

የዘርና የቋንቋቸው የሃይማኖት አዠማመራቸው ልዩ ጥናት ይፈልጋል ፡ ሊቃውንቱ የሐድያ ሕዝብ የኩሽ ዘር ሆኖ ቋንቋቸው ሲዳማ መሆኑን ያመለክታሉ ።

በነርሱና በጐረቤቶቻቸው በጋሎች ወይም በሲዳሞና በወላሞ በከፋዎች መካከል የዘርና የቋንቋ መቀላቀልና መሰባጠር በብዛት ስላለ ብዙ ጊዜ አንዱ በሌላው ስም ይጠራል ። ዛሬ ጉዴላ የሚባሉት እነርሱ ናቸው ፤ ይኸን ሥያሜ ግን አይወዱትም ይባላል ።

በውነትም ጉዴላዎች ከሐድያዎች ሊለዩ ይችላሉ ። ለዓፄ ዓምደ ጽዮን በቀድሞው አማርኛ የተደረሰው ግጥም ፡

“ሐርበኛ ዓምደ ጽዮን
መላላሽ የወሰን . . . . .
ዓምደ ጽዮን ስም የዘራ
በ(ከ) ወጅ እስከ በጠር አሞራ (ቦተር አሞራ) . . . . . . ካለ በኋላ ከዚሁ አያይዞ በ(ከ) ሐድያ እስከ ጉዴላ
በባሕር እስከ ኤርትራ
ዓምደ ጽዮን ስም የዘራ

ስለሚል ሐድያና ጉዴላ ጐን ለጐን የሚገኙ ሁለት ጐሣዎች እንጂ አንድ ጐሣ አያደርጋቸውም (1) ። አቶ ኃይሌ ቡባም በዛሬ ጊዜ የሐድያ ሕዝብ ሊቢዶ ፡ ሻሾን ፡ ሌሞ ሶሮና ባደቾ በሚባሉ ጐሣዎች የተከፋፈለ ሆኖ ግማሹም በከምባታ በወላሞ በአላባ መገኘታቸውን ይገልጻሉ ።

በ፲፭ኛው ዓ. ም. የነበረው አል. ማክሪዚ የሚባለው የዓረብ ጸሐፊ በአበሻ ያሉ የእስላም መሳፍንት ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ የይፋቱን የደዋሮውን የሐድያውንና ሌሎችንም ይጠቅስና የሐድያ ሕዝብ ንጉሥ ብዙ ሠራዊት እንዳለው ወደ ግብፅ ሳይቀር የሚላኩ በግብፆች ዘንድ ተዋሲያ የሚባሉ ብዙ ስልቦች በደንብ እየተሰለቡ የሚሸጡት ከሐድያ መሆኑን ያመለክታል (2) ።

ከቀድሞ ጀምሮ የሐድያ ባላባት ሃይማኖቱ እስላም ከመሆኑ የተነሣ የይፋት ወላስማ ባላባቶች ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ በአሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት ላይ በሸፈቱ ቍጥር አንድ አንድ ጊዜ ከነዚያ ጋር እየተደረበ ማወኩ በየዜና መዋዕሉ ተጠቅሶ ይገኛል ። ሳብር አድ ዲን የወላስማው ባላባት እንዳሁኑ እንደ ግራኝ ጊዜ የቅርብ ጐረቤቶቹን አሳድሞ ባፄ ዓምደ ጽዮን ላይ በተነሣና ጓደኞቹን ሰብስቦ ምክር በጠየቀ ጊዜ አመኖ የሚባለው የሐድያ ባላባት «ለንጉሡ ላምደ ጽዮን አትገብር ፤ ቢመጣብህም ተዋጋው አትፍራው ከሠራዊቱ ጋር

(1) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ገጽ 101
(2) ማክሪዚ ሂስቶሪያ ሬጉም ኢስላሚቲ ኮሩም . . . . የላቲን ትርጉም - ሪንክ ገጽ 14 - 15



የሐድያ አውራጃ ሴት (VIAGENS-COVILHAO)

ISIC

ጨርሰህ ታስገብረዋለህ» ብሎ ለሳብር አድ ዲን (ሰበርዲን) መምከሩን በግዕዝ የተ ጻፈው ያቄ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ያስረዳል (1) ።

የሐድያውን ባላባት ያምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ የሐድያ ንጉሥ ሲለው የቀ ረው ሁሉ ዜና መዋዕል የሐድያ ገራድ ነው የሚለው ። እርሱንም በጋብቻ ዝምድና ለመያዝ ሲሉ ነገሥታቱ ሴት ልጆቹን ወስደው በክርስትና ካስጠመቁ በኋላ ስማቸ ውን ዕሌኒ እያሰኙ ያገቡዋቸዋል ።

ነገር ግን ወጣቲቱ ሃይማኖቷን ለውጣ ክርስቲያን ሆና የንጉሡ ነገሥቱ ሚስት መሆኗ አብዛኛ ጊዜ ሁኔታውን ሳይለውጠው እየቀረ የደዋሮና የሐድያ ባላ ባቶች ብዙ ጊዜ እየገበሩ በሰላም ሲኖሩ በእስላምነታቸው ብቻ እየተሳቡ አንዳንድ ጊዜ ከሚሸፍቱት ከወላስማ ባላባቶች ጋር ከማደም አልተመለሱም ። ምክንያቱም እገዛለሁ ብሎ ላንድ ዓላማ የተነሣ ሰው በፊቱ እንኳን የጋብቻ ገመድ የሥጋ ልደ ትና የደም ጥልቀትም በፍጹም ሊያግደው ስለማይችል በዚሁ አባትና ልጅ ወንድ ማማቾችም ሲጋደሉ ኖረዋል ።

በዚሁ መሠረት ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመናቸው የሐድያውን የገራድ መሐመ ድን ልጅ አግብተው ዕሌኒ ቀኝዕ በዓልቴሐት (የቀኝ ባለቤት) አሠኝተው አግብተ ዋቸው ነበር ። ነገር ግን የሰበርዲን ተወላጅ የሆነው መሐመድ በድላይ የሸፈተባ ቸው ጊዜ የሐድያው ገራድ የሚስታቸው ወንድም ልቡን ከመሐመድ በድላይ (አርዌ በድላይ) ጋር አድርጎ ባንድ ወገን ካንተ ጋር ነኝ እያለ ለርሱ ውስጡን እየላከ በሌላ ወገን ላፉ መጥቼ ልርዳዎ ብሎ ላፄ ዘርዓ ያዕቆብ መላክተኛ ስለላከ ንጉሠ ነገሥቱ አላላኩ የሸንገላ መሆኑን በመረዳት "አይፈርስ ላይ ተዘጋጅተህ ጠብቅ ወደኔ መምጣት አያስፈልግም" ብለው እንደላኩበት ዜና መዋዕላቸው ያመለክታል (2) ። ልጃቸው ዓፄ በእደ ማርያምም የደዋሮውን ባላባት የመሐመድን ልጅ አግብተው እንዳባታቸው እሌኒ ቀኝዕ ባልቴሐት አሰኝተው አግብተው እንደነበረ እኝህም ታላቅ ንግሥት ባፄ ልብነ ድንግል የወጣትነት ዘመን ለመንግሥቱ የሞግዚት እን ደራሴ ሆነው የሠሩትን በምዕራፋቸው አንብበነዋል ።

በዚህ ዓይነት የሐድያ ገራዶች ከጋብቻው ዝምድና ይልቅ ለሃይማኖት ዋጋ ይሰጣሉ ማለት ነው ። ዓፄ ልብነ ድንግል ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ባንድ ሚስት በሰብለ ወንጌል ከመወሰናቸው በፊት የቀድሞው ልማድ አስገድዷቸው የሐድያውን ገራድ ሴት ልጅ ለማግባት ካገሯ ካስመጧት በኋላ በገጣጣነቷ የተ

(1) ለንጉሠ ሐድያ ዘስሙ አመኖ ወይቤሎ ኢትሑር ኀበ ንጉሠ ጽዮን (ዓምደ ጽዮን) ወኢተሀቦ ጋዳ ወሰበ ይመጽእ ኀቤከ ኢትፍርሆ እስመ ይገብእ ውስተ እዴከ ወአንተ ተሐልቆ ምስለ ሠራዊቱ ያቄ ዓምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ . . . . . ገጽ 286 ። የኢትዮጵያ ነገሥታት አንዳንድ ጊዜ ንጉሠ ጽዮን (በአክሱም) ይባላሉ ። .

(2) ወሐድያ ገራድሰ ለአከ ኀበ ንጉሥ እንዘ ይብል ለእመ እመጽእ ከመ እትራድአከ ፊት ቃለከ ኀቢየ ወኀበ ውእቱኒ አርዌ በድላይ ለአከ እንዘ ይብል "አነኒ ሐበርኩ ምስሌከ እመጽእ ለተራድአ ትከ ፡ . . . . ወውእተ ጊዜ ለአከ ኀቤሁ ንጉሥን ዘርዓ ያዕቆብ እንዘ ይብል ዝየሰ ኢትምጻእ ባሕቱ ንበር ሀገረ አይፈርስ በተደልዎ . . . . . ያቄ ዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 58 - 59

ኑሣ እርሳቸው ከርሷ መጋባትን ትተው ላንዱ ቢትወደዳቸው እንደዳሯት አልቫ ሬጽ የጠቀሰውን ደግመን እናስታውሳለን ። ከዚያ አያይዞ ለጋብቻ የመጣችው ሴት እኅቷ የሐድያ ንጉሥ ሚስት የነበረች የባልዋ ወንድም የነበረ ሰው ግዛቷን ለመውሰድ ስለ አስፈራራት ለአቤቱታ ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ወዳዬ ልብነ ድንግል መምጣቷን ፥ ሴት ወይዘሮዋም ላቤቱታ በመጣችበት ጊዜ ፶ በበቅሎ የተቀመጡና ፶ እግረኞች አጅበዋት እንደነበረ በመጣች በ፫ኛው ቀን ንጉሡ ነገሥቱ ተቀብለው ጉዳይዋ እንደሚፈጸምላት እንደነገሩዋት ይገልጻል (1) ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ግራኝ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ንጉሡ ነገሥቱን በሽምብራ ኩሬ ባሸነፈበት ወቅት ከዚያ ወደ ቤተ አምሐራም ሄዶ ከተመለሰና ደብረ ብርሃን ከነአዶሌ ተገናኝቶ ብዙ ቀን የተቀመጠ ጊዜ የሐድያው ገራድ ገሥግሶ ወደ ግራኝ መጥቶ በመግባት ታማኝነቱን አልገለጸም ። በችኮላም ይኸን ያላደረገበት ምክን ያት ባያት በቅድም አያቶቹ ዘመን እንደተለመደው ግራኝ ዘርፎ አቃጥሎ ወደ አገሩ የተመለሰ እንደሆን ወይም ተመልሶ በክርስቲያኖቹ የተሸነፈ እንደሆን በክር ስቲያኖቹ በኩል ከዳተኛ ተብሎ መጉላላት እንዳይደርስበት ለጥንቃቄ ያደረገው መሆን አለበት ። ነገር ግን በገሀድ ይሁን በስውር ቀደም አድርጎ በመልከተኛ አማ ካይነት ሳይስማማ የቀረ አይመስልም ። የሆነ ሆኖ አሁን የግራኝ የጦር አለቆች በሐድያ ግራና ቀኝ ያለውን የደዋሮን ፤ የፈጠጋርን ፤ የከምባታን ፤ የገንዝን (ግንጭ) የወጅን ፤ የጉራጌን አውራጃዎች እየያዙ ሲያስገብሩ ሕዝቡን ሲያሰልሙ ራሱ ዋናው ገዥ ግራኝ አህመድ ከጉራጌ አገር ወደ ዟይ መሄዱን ትቶ ወደርሱ አገር ስለ ሄደ ተሰልፎ መጥቶ በደስታ ተቀበለው የአቀባበሉን ዝርዝር ከዓረብ ፋቂህ መጽ ሐፍ ከዚህ እንደሚከተለው ማንበቡ ይጠቅማል ።

«ይማም አህመድ በበኩሉ ከነበረበት ከጉራጌ ተነሥቶ ከዟይ ሐይቅ በላይ በኩል ሠፈረ ። የዚህ የሐይቅ ወሀ በጣም ጥሩ ነው ። በታንኳ ሦስት ቀን ያስሄዳል ። በውስጡ ሦስት ደሴቶች አሉ ። በያንዳንዱ ደሴት ፫ አብያተ ክርስቲያናት አሉበት ይማም ታንኳ አሠርቶ ሊገባ አስቦ ነበር ። ነገር ግን እስላሞቹ በቂ ስንቅ የለንምና ሐይቁ ይቅርብን ይልቅስ ወደ ሐድያ እንሂድ ፤ የሐድያ ሰዎችም የሐይቁን ክርስቲ ያኖች ለማሸነፍ ይበቃሉ ብለው ስለመከሩት ዟይን ተወና ወደ ሐድያ ደረሰ ። የሐ ድያ ሹም ወደ ይማም መጣ ። እርሱም ላበሻው ንጉሥ የሚገብር እስላም ነው ። በያ መቱ እንደ ልማድ አንዲት ወጣት ልጅ ለንጉሡ እየገበረ ወጣቲቱ በክርስትና ትጠ መቃለች ። ይህ የሐድያ ባላባት ጦሩን ይዞ ወደ ይማም መጣና እኔም እንደናንተ እስላም ነኝ ለፊቃዳችሁ እታዘዛለሁ ብሎ ተናገረ ። አህመድም በደህና ተቀበለው ።

እርሱም እስላሞቹን በደንብ አስተናገዳቸው ። ይማም ለርሱ የሚያምር ሽል ማት ሸልሞ ከርሱ ጋር ለመጡትም ላገር ሹማምንቶች ልብስ አደላቸው ። ወዲያ ውም እናንተ እስላሞች ሆናችሁ ላበሻው ንጉሥ ቆንዦ ልጃገረዳችሁን የምትገብ ሩት እንደምን ነው ብሎ ቢጠይቃቸው ከኛ ይበልጥ ንጉሡ ኃይል ስለነበረው ይኸን

(1) አልቫሬዝ በነአቶ ግርማ በሻህ ትርጉም ምዕ. 118

እንድናደርግ አባቶቻችንን አስገደደ ፣ መከላከያ ሰይፍም እንዳንይዝ ሌጣውን እንጂ እተጫኑ ፈረስም ላይ እንዳንወጣ ተከልክለን እንኖራለን ። በዚህም ላይ በያመቱ አንዲት ወጣት ልጅ እንድንገብር አስገድዶን ፤ እኛንም እንዳይገድለንና መስጊዳችንን እንዳያፈርስ በመፍራት እንገብራለን ። የግብሩን ገንዘብና ወጣቲቱን የሚረከበው ሰው ሲመጣ ወደ ውጭ አውጥተን አካሏን እጥበን በጨርቅ ገንዘን በቃሬዛ አድርገን እንደሞተች ቆጥረን ስለርሷ ጸልየን እናስረክበዋለን ። በዚሁ ዓይነት አባቶቻችንም አያቶቻችንም ሁሉ ያደርጉ ነበር ። አሁን ግን ልዑል እግዚአብሔር እስላሞቹን አመጣልን ፡ ጌታችን የነበረውን (ንጉሡን) አባረራችሁ ፣ ወታደሩንም ጨረሳችሁ ከእንግዲህ ወዲያ ከእናንተው ጋር ሆነን . . . . . . እንወጋቸዋለንና ሊያሠቃዩን አይችሉም . . . . . ብለው መለስለት ይማምም አይዟችሁ ኃይላችሁን ከኛው ጋር ደርቡት አላቸውና እነሱም እሺ ብለውት በነርሱ አገር ፰ ቀን ከተቀመጠ በኋላ የሐድያውን ባላባት እንደያዘ ከሐድያ ወደ አይፈርስ ሄዶ ተቀመጠ . . . . . .» (1) ።

በዚህ አነጋገር የሐድያዎቹ ሹማምንት ለግራኝ አህመድ ሰይፍም እንዳንይዝ በፈረሳችንም ሌጣውን እንድንቀመጥ እንጂ ኮርቻ እንዳንጭን ተከለከልን ያለው ምናልባት እውነት ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም የሐድያው ገራድ ወዲህ ላማቹ ወዲህ ለገኘው ንጉሠ ነገሥት በመታመን ፊንታ ባለፈው እንዳመለከትነው በፊትይፋት በኋላ ሐረር የተቀመጠው የአዳል ሱልጣን በሸፈተ ቍጥር ወደዚያ እየተደረበ መሸፈት ስለአስለመደ ባገሩ ላይ ሰይፍ ጨብጦ ኮርቻ በፈረስ ጭኖ ሊዋጋ የሚችል ወታደር እንዳይመለምል በማለት መንግሥቱ ይኸንን እርምጃ ወስዶ ይሆናል ።

በተረፈ ሌላው ንግግር ሁል ጊዜ አንድ ሕዝብና ባላባት በፊተኛው ገዥ ዘመን ባይጠቃም ነዋሪውን የመንግሥት መሪዎች አሸንፎ አገር ላይ አዲስ ገዥ በገባ ጊዜ እርሱን ለማስደሰት ጭምር እየተባዛ የሚነገር ንግግር ነው ።

ኢጣልያ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ኢትዮጵያን ወርሮ በገባበት ጊዜ አንዳንዱ ባለሥልጣን ከጃንሆይ ጋር ያልነበረውንም የነበረውንም ጠብ አጋኖ በማሳየት ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ለመወዳጀት ይጥር ነበር ። ንጉሡ እኔን ስለማይወዱኝ አግዘውኝ ፣ ሽረውኝ ይኖሩ ነበር ወይም ሽረው ሊያግዙኝ ሲሉ ኃያሉ የኢጣልያ መንግሥት ደረሰልኝ የሚለው ኢትዮጵያዊ መኰንን አልፎ አልፎ ይታይ ነበር ። በዚሁ አንጻር በእንግሊዝ ጦር እርዳታ ጃንሆይ ባሸናፊነት አዲስ አበባ ገብተው በዙፋናቸው በተቀመጡበት ሰዓት ሁሉም የኢጣልያንና የፋሽስት ጠበኛና ባላጋራ ሁሉም አገር ወዳድና ነፃነት አፍቃሪ ሆነ ። አገር የበደለውም ባንዳውም ሁሉም ስለነፃነትና ስለጃንሆይ መመለስ የሚጸልይና የሚሳል ሁሉም ፋሽስትንና የጣልያንን መንግሥት ረጋሚና ወንጃሊ ሆነ ። እንዱ በኢጣልያ አገዛዝ ሥር አብሮ እየሠራ የቆየ ኢትዮጵያዊ ለትምክህት የሚበቃ የስደት ፣ የእሥራት ፣ የአርበኝነት ምክንያት ስላጣ ጃንሆይ ከገቡ በኋላ የሕይወት ታሪክህን ሙላ ተብሎ ሲሞላ «ያገሬ ነፃ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 371 - 373

ነት እንዲመለስ በልቤ እየጸለይሁ ላዩን አብሬ በምሠራበት ጊዜ ኢጣልያኖቹ በክፉ ዓይናቸው ይመለከቱኝ ነበር» ብሎ ሞላ ይባላል ።

እንኳን ኢትዮጵያውያኑ ራሳቸው ኢጣልያኖቹ በአምስቱ ዓመታት በኢጣልያንነታቸው ፤ በፋሽስትነታቸው እየተመኩ በእጃቸው የወደቀውን አርበኛ ሲገድሉ፤ ሰላማዊውን ሕዝብ በማሸበር ፥ በማሰር ፥ በመፍታት ዓይናቸውን እያቀሉ ጠረጴዛ በቡጢ እየመቱ እንደግሥላ እየተቆጡ የሚያጉላሉት ሁሉ ጃንሆይ ከተመለሱና ሥልጣን በኢትዮጵያውያኑ እጅ ከገባ በኋላ ሁሉም ሰላማውያንና ትሁታን ሆኑ፤ ሁሉም የሙሶሊኒና የፋሽስት ጠበኛ ሁሉም የዘመተው እየተገደደ እንጂ በፈቃድ አለመሆኑን ይገልጽ ነበር ። በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ያለው የመኖር ጣጣ ብዙውን ጊዜ ይኸን በመሰለ አኳኋን አሳቡንና አንደበቱን እየለወጠ አብሮ የመኖር ዘዴ እንዲፈልግ ሲያስገድደው ይታያል ። የሐድያ ገራድም በሰላሙ ጊዜ ባዬ ልብነ ድንግልና በጦር አለቆቻቸው ፊት ምናልባት ከወደ መዠመሪያ ጊዜ ላይ የሃይማኖት ወገኖቹን የሐረሩን ሱልጣን ኡመር ዲንንና አህመድ ግራኝን ሳያማ በአነጣሡም ሳያወግዝ አይቀርርም ።

አሁን ወጣቲቱን አጥበን ገንዘን እንደሞተች ቆጥረን ወደ ንጉሡ እንልካታለን ያለው ንጉሡ ነገሥቱ በክብራቸው በነበሩበት ሰዓት መታጠቧ ለንጽሕና የርዓም ምርጫ እንደ ዕድል ተቆጥሮ ሳይኰራበት አይቀርም ። ባሁኑ ጊዜ የአነጋገሩ አቅጣጫ መስመሩን ቢለውጥ ባንድ ወገን የሃይማኖት በሌላ ወገን ያድር ባይነት ጠባይ የሚፈጥረው ምክንያት ስለሆነ አይፈረድበትም ። ክርስቲያኖቹ እነሃይቢ እነአናንያ እነወናግ ዣን እነስምዖን (ሲሙ) የክርስትና ሃይማኖታቸውን ለውጠው ክርሱ የበለጠ ወገናቸውን እንደበደሉ አንብበናል ።

የሆነ ሆኖ የሐድያ ገራድ በዚሁ በእስላምነቱ ምክንያት ለግራኝ እንደገባ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ሴት ልጁን ሙሪያስ የምትባለውን ለአሸናፊው ለግራኝ አህመድ እህቱን ለታማኙ ለአብድ ኢን ናስር ድሮ በመዛመድ ተስማማ ። ከዚህ በኋላ ለግራኝ ፈጽሞ ታማኝ አገልጋይ በመሆን ከእህቱ ባል ከአማቹ ከአብድ ኢን ናስር ጋር ሆኖ የባሌውን ዠግና አዝማች አዳሉን ሊወጋ ሄደ (1) ።

## ምዕራፍ ፳፪

## የዘላህ (ባሌ) ጦርነት (፲፱፻፳፱ ዓ. ም. ነሐሴ)

## የዠግናው የአዝማች አዳሉ ውጊያና አሟሟት

ኢትዮጵያ በዚህ በመከራና በጦርነት ሰዓት ካፈራቻቸው ከዋነኞቹ ዠግኖች መካከል ሆኖ የሚቆጠረው አዝማች አዳሉ ነው ። ይኸንንም ዠግና የጦር መኰንን ያገራችን ጸሐፍ በፍጹም ስለማያነሣው እንኳን አስደናቂ ጀብዱውን ትክክለኛውን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 376 - 377

ስሙንና የማዕርግ ስሙን ስለማናውቅ ይኸው የዓረቡ ጸሐፊ አንድ ጊዜ አዳሊ አንድ ጊዜ አዳሉ ስለሚለው የመጨረሻው አባባል ለኢትዮጵያ ለዚህ ዘመን የጦር አለቆች አጠራር የቀረበ ስለሆነ አዝማች አዳሉ እያልን ጽፈነዋል ። በዚያን ዘመን አጠራር እስላም ሰገድ ይልና ባጭሩ እስላሞ ይላል በአይፈርስ እየተዋጋ የሞተውን ራስ እስላም ሰገድን እናስታውሳለን ። የከዳተኛው የወናግ ዣን ልጅ እርሱም ከዳተኛ የሆነው ሙሉ ስሙ ስምዖን ሲሆን ባጭሩ ሲሙ ይባላል ። በዛሬም ዘመን ሠርፀ ድንግል የሚባል ሰው ባጭሩ ሠርፁ ይባላል ።

አዝማች አዳሉም ምናልባት በአዳል አገር ብዙ ጊዜ ጦርነት እየተደረገ በአዳሎች ላይ ለሠራው ጀብዱ ሕዝብ ወይም የርሱ ጭፍሮች "አዳል ሰገድ" ያሉትን ሕዝብ አሳጥሮ አዳሉ ይለዋል ማለት ነው ። ይኸም ለዠግንነቱ የወጣለት የቅጽል ስም ስለሆነ ሌላ የመጠሪያ ስም አያጣም ። የትውልድ አገሩም በትክክል አይታወቅም ። ዓረብ ፋቂህ የባሌው ይለዋል ። ነገር ግን በተወላጅነት ወይም በሹመት የነበረበት መሆኑን አይገልጽም ። ነገር ግን ዘመንክር የሚባል ልጅ ስላለው አዳሉም ዘሩ አማራ ሆኖ በሹመት ባሌን የገዛ ወይም የባሌን ጦር የመራ ይመስላል ።

ይህ የጦር መኰንን አሁን ሲዋጋ የምናየው ምንም የማሸነፍ ተስፋ በሌለበት ሰዓት ነው ። የንጉሡ ነገሥቱ ኃያላኑ የጦር አለቆች ግማሾቹ በጦር ሜዳ ወድቀዋል ግማሹ በንጉሡ ዙሪያ በጐጃም ወይም በቤጌምድር ይገኛል ። የቀረውም ለግራኝ እየገባ ሰልሞ ተቀምጧል ። ነገር ግን በዚሁ ተስፋ አስቆራጭ ሰዓት ፤ ንጉሥ በሌለበት የጠላት ጦር በያለበት በሰፈነበት ሰዓት እንደ ግራኝ ያለውን የኃይለኞች ኃይለኛ አሸንፎ ለመመለስ ያለው ተስፋ በመነመነበት ሰዓት እርሱ በግራኝ ዋና የጦር አለቃ በወዚር አዶሌ የሚመራውን ጦር ሊወጋ ይዘጋጃል ።

ISIC

የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ማይጨው ተሸንፎ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሎንዶን ከሄዱ ጣልያን አዲስ አበባንና ብዙ አውራጃዎችን ከወረረ በኋላ ቀደም ብሎ እነደጃች ባልቻ ከዚያ እነደጃች ፍቅረ ማርያም ከዚያ በሸዋ እነ ራስ አበበ አረጋይ በቤጌምድር እነራስ ውብነህ (አሞራው) በጋላ አገር እነደጃች ገረሡ በሶዶ እነደጃች በቀለ ወያ ለአርበኝነት ከተሰማሩት ጋር የዚህ ሰውዬና እርሱን የመሰሉት ባሁኑ ሰዓት የሚዋጉት በአርበኝነት መስመር ይመሳሰላሉ ። ሁኔታው ሲመዛዘን ግን ከኢጣልያው ጊዜ አርበኝነት ይልቅ የዚህ የግራኝ ጊዜ አርበኝነት የበለጠ አስቸጋሪነት አለው ። የኢጣልያ ወታደሮችና ሹማምንቶች ምንም እንኳ የባንዳ ወታደር ቢኖር ከባሕር ማዶ የመጡ ለአገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ ሲሆኑ የግራኝ አህመድና የተከተለው ሕዝብና ሹማምንት ከቅርቡ የመጣ ከገባለት የክርስቲያን ሕዝብ በቀር ያገሩን መውጫና መግቢያ የሚያውቅ የቅርቡ የአዳልና የሱማሌ ሕዝብ በወዲህ ከነዋሪው ከደዋሮ ከይፋት ከባሌ ሕዝብ ጋር በሃይማኖት የተሳሰረ ስለሆነ ይኸው ራሱ የግራኝን ድል አቃንቶለታል ። አንድ ግዕዝኛ ጽሑፍ ግራኝ ደዋሮን የወረረ ጊዜ ሕዝቡ ግማሹ የሰይፉን በትር በመፍራት የቀረውም አብዛኛው ሕዝብ በሃይማኖት ስምም ስለሆነ የርሱን ሃይማኖት የሚያፈቅረው እንደተቀበለው ባለፈው ያነበብነው ትዝ ይለናል ።

የሆነ ሆኖ እውነተኛ አርበኛና ዠግና የሚባለው ከበላይ መሪ ሥር ሆኖ በደ ረጃ ጦር በስንቅ አቀባይ መካከል ሆኖ የሚዋጋው አይደለም ፤ በዚህም ውስጥ ሆኖ የተሠራው ጀብዱ ያው የጀብዱነት ዋጋውን አይለውጥም ። ነገር ግን ይኸ ሁሉ ከጠፋና ከተደመሰሰ ነዋሪ ጦር ከፈረሰ ጠላት አገርን ከወረረ በኋላ የፈረሰ ጦር አቋ ቁሞ ለአልሁና ለወኔው ብቻ ሲል እምቢ ለጠላት አልገዛም ሃይማኖቴን አልለው ጥም ብሎ የሚዋጋ ንጹሕና ነቅ የሌለበት አርበኛ ነው ።

ገባሚው ማን መሆኑን የማላውቀው ኢጣልያ ከወጣ በኋላ ለነዚህ ሰዎች ሲገ ጠም የሰማሁት ግጥም ትክክለኛና ግልጽ ነው ።

"ሰው ማለት ሰው ማለት
ሰው የሚሆን ነው ሰው የጠፋ ለት"

አዝማች አዳሉ ባለፉት ዓመቶች የዋለባቸውን የጦር ጉራዎች አናውቅም ከዚህ በፊት በንጉሡ ትእዛዝ በደዋሮ እስላሞቹ የሚተላለፉበት መንገድ ይቆፈር የተባለ ጊዜ ከራስ ወሰን ሰገድ ልጅ ከባሕር ሰገድ ጋር ሆኖ አስቆፍሯል ፤ ወሰን ሰገድ ከሞተ በኋላ በደዋሮ ተሾሟል ። እንደ ዓረብ ፋቂህ አነጋገር ከዚህ በፊት በባሌ አንድ ጊዜ የተዋጋ ይመስላል (1) ።

አሁን ግን በዚህ በባሌ ዙሪያ የግራኝ ጦር አጥለቅልቆ አውራጃውን ሁሉ በወ ረረበት ሁሉም ተስፋ እየቆረጠ ሰልም በገባበት ሰዓት እርሱ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ሊዋጋ ትልቅ ዝግጅት አድርጓል ፤ በተጉለት የነተከለ ጊዮርጊስ ሞት በይ ፋት የነራስ ነቢያት ሽሽት በዝቋላ የነተሰፉ በወጅ የነእስላም ደሀር መገበር የነአዝ ማች ዮናዳብ በእንጉትት አድርገው ወደ ንጉሡ የመሸሽ ሁኔታ ሕዝቡ ሁሉ ከነሾማ ምንቱ ግማሹ ወደ ዋንዩው ወደ ግራኝ የቀረውም ወደነአቡበከር ወደነኤሚር ሁሴን እየገባ መስለሙ በቁርጥ ለውጊያ የተነሣበትን መንፈስ አላላውም ።

የዚህን የሰውዩና የጓደኞቹን ውጊያና ዠግንነት ወገኖቹ አባቶቻችን ያለፉ ትን የጠላት ጸሐፊ አልዘነጋውምና በቀጥታ ከተለመደው ከዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ በሚቀጥለው እንመልከት ።

«ይማም ጎይታ አላህ መጀን የሚባለውን የሐድያ ባላባት መግባቱን ለኤሚር ሑሴንና ለወዚር አዶሌ ይነግራቸው ዘንድ ወደ ጀደራ (ገደራ?) ላከው ። እርሱም ወደነርሱ ለመሄድ መንገድ ዠምሮ ጋንቡራ ላይ ሲደርስ አዝማች አዳሉ ጋቱር ሄዶ ከአምሐና ከፋትኤል ጋር ተገናኘና የእስላሞች ምን ወሬ አለ ፤ ያሉበትስ ወዴት ነው ፣ እናንተስ በከንቱ ለምን እዚህ ተቀመጣችሁ ብሎ ቢጠይቃቸው ኤሚር ሁሴ ንና ወዚር አዶሌ ጀደራ ናቸው ኤሚር አቡበከር ቀጢን ወደ ጂራውራሪ ሄዷል ይማም አልመጣም ፤ እርሱም ያለው በሐድያ ነው ይባላል ብለው መለሱለት ። እን ግዲያውስ ይህ የምትሉት እውነት ከሆነ ሌሊቱን ተጉዘን በሳሪ በር እንለፍና ሲነጋ ኤሚር ሑሴንን ጦርነት እንግጠመው ። በኋላ ግን ይማም መጥቶ ከነርሱ የተደባ ለቀ እንደሆነ ለመዋጋት ይቸግረናልና አሁኑን በተለያዩበት ሰዓት ሄደን ብንዋጋ ይሻላል አላቸውና ፫፻ ፈረሰኛ ፮ሺ የእግረኛ ጦር ይዘው ጉዞ ዠመሩ ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 175 - 178 - 343 - 342 - 344 . . . . . ።

አላህ መጀን መልክቱን ለማድረስ በሳሪ በር አድርጎ ሌሊት ሲሄድ የርሱ ሰዎች አምሐ በተኝ ፋኑኤል በግራ ፤ አዝማች አዳሉ በመካከል ሆነው ብዙ ጦር ይዘው ሲጓዙ አዩዋቸውና ወደኋላ ለነበረው ላለቃቸው ለአላህ መጀን ይኸውና የጠላት ጦር ከኋላችን መጣ ያለን ፳ ፈረሰኛ ብቻ ስለሆን ይኸን ጦር መመለስ አንችልም ። ስለዚህ ወደ መጣንበት አገር ወደ ይማም ዘንድ እንመለስና ነገሩን እንንገረው አሉት ። እርሱ ግን አገሬን ትቼ እዚህ የመጣሁት ለዚህ ለተቀደሰ ጦርነት ሰማዕት ለመሆን ነው ። በዚህም ላይ ይማም የሰጠኝን ሰንደቅ ዓላማ ይገፍ ሳልዋጋ እሸሻለሁን ፤ እናንተ ግን መሸሽ ከፈለጋችሁ ሽሹ ። መንግሥተ ሰማያትን ፤ ዓይናቸው የጠቋቆረውን የሰማይ ቆንገዦችን ፈልጋችሁ እንደሆነ ተከተሉኝ ጦርነቱንም የምገርምረው ራሴ ነኝ አላቸውና ጥሩሩን (የብረት ልብሱን) ለብሶ ሰይፉንታጠቀና አፈረሱ ላይ ወጣ የፈረሱም ስም ለዛዝ ይባላል ። ጓደኞቹን ዘሐርቡይ አሊን ፤ አቡበከር ቤን አርሳን ፤ ካሌድ ቤን አድፋህን . . . . . . በርቱ እያለ እያጽናና ወደ ጠላቶቹ ሄደ ። የቀረው ጦሩ ከአውራይ ኑር ጋር ባንድ ወገን ተጓዘ እስላሞቹ ክርስቲያኖቹን ባዩ ጊዜ አላህ መጀን እኔ የአህመድ ልጅ ነኝ ይኸን ነው የምፈልገው ብሎ ፫ ጊዜ ጮኸ (1) ና በአለንጋ እየመታ ባንድ ጊዜ ፈረሱን ፳ ከንድ እያዘለለ አስጋልቦ እክርስቲያኖቹ መካከል ገባ . . . . . . እየተማታ ፯ ክርስቲያኖች ከገደለ በኋላ እመካከል ከነበረው ከአዳሉ ጋር ተገናኝተው ተጋጠሙ ሁለቱም በጦር ሲደባደቡ አላህ መጀን አዳሉን ልበ[illegible]በጦር ወጋው ነገር ግን አዳሉ የለበሰው ኃይለኛ ጥሩር ስለነበረ ጦሩ እጥሩሩ ውስጥ ገብቶ ተሸነቀረና ለመምዘዝም ቢሞክር ጦሩ ተሰበረ ፤ ከዚያ ሰይፉን ከአፎቱ አውጥቶ ወደ አዳሉ ቢመለስ አዳሉ ከጦሩ ጋር ተደባልቋል ። ቢሆንም የቀሩትን ክርስቲያኖች እያለፈ ከፊቱ ሲፈጅ ጋሻና ጦር የያዙ የእግረኛ ወታደሮች ከኋላው በጦር ወርሡረው ፈረሱን ቢመቱት ጦሩ ሆዱን ቀዶ ወጣና ፈረሱና አላህ መጀን ተያይዘው ወደቁ ፤ ከዚያ አላህ መጀን ሰይፉን በእጁ እንደ ጨበጠ ከወደቀበት ለመነሣት ሲሞክር አዳሉ መጥቶ በኃይል በጦር ወጋውና ገደለው ። ካሌድ ቤን አድፋህ ከፋኑኤል ጋር ተጋጥመው በሰይፍ ሲዋጉ ክርስቲያኖቹ ተሰብስበው ገደሉት . . . . . . አቡበከር ቤን አርሣም እንደዚሁ ሞተ ። ዘሐርቡይ አሊን ግን ክርስቲያኖቹ የፈረሱን ቋንዣ መትተው ጥለው እርሱንም በጦር ወጋግተው ሞተ ብለው ጥለውት ከሄዱ በኋላ ድኖ ተነሥቶ በኋላም በትግሬ ጦርነት ለመካፈል ችሏል ።

አውራይ ኑርና ጓደኞቹ ግን የአላህ መጀንን እክርስቲያኖቹ መካከል መግባት (ገብቶ መሞት) ሲያዩ ሸሽተው ወደኋላ ሲመለሱ ክርስቲያኖቹ እየተከታተሉ ፬ ፈረሰኛ ፰ እግረኛ ገድለውባቸው ፈረሶቻቸውንም ማረኩባቸው ።

ኢሚር ሑሴንና ወዚር አዶሌ የዚህን ወሬ በሰሙ ጊዜ ብዙ የፈረሰኛ ጦርነት ወደተደረገበት ሥፍራ ልከው የአላህ መጀንን ሬሳ አስቀበሩ ።

በበኩሉ ይማም አህመድ ከነበረበት ከአይፈርስ ወደ ሳዱቃህ መጣና ሠፈረ

(1) ምናልባት እኔ የአህመድ ልጅ ይችን ይወዳል ያለውን አሳቡ ለሙሴ ባሴት ረኋ በግልጽ አልገባቸው ይሆናል ።

በዚያም ገበሬዎች ተይዘው እፊት ቀረቡና ስለ ክርስቲያኖች ወሬ ታውቃላችሁን ተብለው ቢጠየቁ አዎን እናውቃለን ጋቱር የነበሩት ክርስቲያኖች ወደ ኤሚር ሑሴን . . . . ሲመጡ አንተ የላከሃቸውን እነአላህ መጀንን በሳሪ ላይ አግኝ ተው ተዋጉዋቸውና ገደሉዋቸው ። ከዚያ በኋላ ክርስቲያኖቹ ተመልሰው ወደ ጋቱር ሄዱ ብለው መለሱ ይማም ስለአላህ መጀን ሞት እያዘነ ካሳዱቃህ ወደ ዳንቅ ሄደ ። ሰዎች ይማም ራሱ ጦሩን ይዞ ሊወጋችሁ መጣ እንደጦር አለቆቹ እንደ ኤሚሮቹ አይምሰላችሁ ብለው ለክርስቲያኖቹ ነገሩዋቸው ። ስለዚህ ክርስቲያኖ ቹም ስለፈሩ ከጋቱር ወደ ሌላ አገር ሄዱ ።

ይማም ደግሞ ከዳንቅ ወደ ጋቱር ጠረፍ መጣ . . . . . . ከዚያ ቀጥሎ ሰበሩ ወደ ይማም ዘንድ መጣና የአዳሉን ወሬ አወራለት ወዳንተም የመጣሁት ከአዳሉ ተደብቄ ነው ብሎ ገለጸለትና በይማም አማካይነት ሰለመ ። ሲሰልምም ከእግዚአብ ሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም መሐመድም የእግዚአብሔር ነቢይ ነው ለርሱም ከእ ግዚአብሔር በረከትና ደህንነት ይውረድለት የሚለውን ቃል ተናገረ ።

ከዚህ በኋላ ይማም የባሌን ግዛት ላንተ ሰጥቸሃለሁ ብሎ ለወዚር አዶሌ ሰለላ ክበት ወዚሩ ስመ ጥሩ ወታደሮቹን እነአብሳማ ኑርን ፣ ወዚር አባስን ፣ ገራድ አህ መድ ጎይታን አውራይ ቃት ዑመርን ፣ ገራድ አህመዱሽን ፣ ፋራቃሃም ሳቱን ፣ አውራህ አህመድን ፣ ሐመድ ሱሃህን ይዞ ወደ ባሌ ጉዞ ገሠመረ ። ቀጥሎ የባሌው ገዥ (አዳሉ) ብዙ ጦር እንደሰበሰበ ማለትን ስለሰማ አብድ ኢን ናስርንና አማቹን (የሐ ድያውን ባላባት) ሄዳችሁ ወዚር አዶሌን እርዱት ብሎ ላካቸው ተደባለቁና ሁሉም ባንድነት ሆነው በሐድያ በኩል ዋቤን ተሻግረው ወደ ባሌ ሄዱ ። መሪያቸ ውም በቅርብ ጊዜ የሰለመው ሰበሩ ነበር ። ጓደኛው የወናግ ዣን ልጅ ሲሙም (ስምዖን) መጥቶ ተደባለቀና ሰለመ ። ከዚያ ወዚር አዶሌ አዝማች አዳሉ ወዴት አገር ይገኛል ብሎ ቢጠይቀው በዛላህ አገር ይገኛል ብሎ መለሰለት ። ከዚህ በኋላ ሰበሩና ሲሙ የሚባሉት ሹማምንት እፊት እፊት እየመሩ ተጉዘው የእስላሞቹ ጦር ዘላህ አጠገብ ሠፈረ ። በዚህ ጊዜ ሲሙ ወደ ወዚር አዶሌ ሄደና «ከእስላሞቹ ጋር ልትዋጋ አትችልም ፣ እስላሞች የብዙ አውራጃ ጌቶች መሆናቸውን ሰምተሃል ሰው ሁሉ እየገበረ በጸጥታ ተቀምጧል የሀበሻም ሕዝብ አጋማሹ ሰልሟል ፣ ንጉሡ ከነ ጦሩ ሸሽቷል ። አሁንም አንተ እስላም ሁን ፣ ሃይማኖቴን አልለውጥም ያልህ እን ደሆነ ለፈረሱም ለጦሩም ስንቅ እየሰጠህ ግብርም እየከፈልህ ተቀመጥ ይኸን ሁለ ቱን ውል (ከ፪ አንዳቸውን) እምቢ ያልህ እንደሆነ ለጦርነት ተዘጋጅ» ብዬ ለአዝ ማች አዳሉ ላላክበት ብሎ አስፈቅዶ ይኸንኑ ላከበት ። አዳሉም ከመልክተኛው አፍ ይኸንኑ በሰማ ጊዜ ስንት ይሆናሉ እስላሞቹ ብሎ ቢጠይቀው ደንበኛው የእስ ላም ጦር ፭፻ ፈረሰኛ ነው በተረፈ በቅርብ ጊዜ እየሰለመ ተከትሎ ሊወጋህ የመ ጣው የኢጅጁ ፣ የደዋሮ ፣ የወጅ ሕዝብ ቍጥር የለውም እጅግ የበረከተ ነው ብሎ መለሰለት ። ከዚህ በኋላ የእስላሞችን ብዛትና ኃይል ብትነግረኝ ከምንም አልቆጥ ረውም ፣ ግብርም አልገብርም እስላም ሁን የምትለኝም አይታሰብም ፣ ከመሰለም ስለአገሬ እየተዋጋሁ መሞትን እመርጣለሁ ብሏል ብለህ ለጌታህ ለሲሙ ንገረው

ብሎ መላክተኛውን መለሰው ። መላክተኛውም መጥቶ ለሲሙ መልሱን ስለነገረው ሲሙ መላክተኛውን እወዚር አዶሌ ዘንድ አስገብቶ አነጋገረው ።

በማግሥቱ ሒት እስላሞቹ ጸሎታቸውን ከአደረሱ በኋላ ለጦርነት ተዘጋጅተው ሰንደቅ ዓላማቸውን እያውለበለቡ ጉዟቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። የባሌው አዝማች አዳሉም በበኩሉ ሴቶቻችሁን ፣ ልጆቻችሁን ከየሥፍራው አስመጥታችሁ ይዛችሁ እስላሞቹን ለመውጋት ተጓዙ የሚል ቃል በየሠፈሩ አስለፈፈ ። ሹማምንቱም ተሰብስበው ወደርሱ መጡና ምነው ሴቶቻችሁንና ልጆቻችሁን ይዛችሁ ተዋጉ ብለህ አዘዝኸን አሁንም ሴትና ልጆቻችን በየተራራው እናስቀምጥና እኛ ከፊትህ እንዋጋ ብለው ቢለምኑት አይሆንም ሴቶችና ልጆቻችሁን አስመጡ እኔም የራሴን አስመጣለሁ እያንዳንዱም ሲዋጋ ቤቱ ሰቡን ከኋላው ያስቀምጥ ወደኋላውም ሲሸሽ ሚስቱን ሲያይ እያፈረ ጠንክሮ ይዋጋል እንጂ አይሸሽም ። ሚስቶቻችሁን እሌላ ዘንድ አስቀምጣችሁ ከተዋጋችሁ በኋላ ብትሸሹ የምታገኙት አንዳች ደህንነት የለም ። ይልቅስ ላገራችሁ ፣ ለሚስቶቻችሁ ለልጆቻችሁ ሙቱ ብሎ መለሰ ።

ሹማምንቱም ይኸን የሚያበረታታ ቃል ከሰሙ በኋላ ሚስትና ልጆቻቸውን አስመጥተው ለጦርነት ተሰለፉ ። እስላሞቹም እንደነርሱ ተዘጋጅተው ወደነርሱ ይጓዙ ገመር የሁለቱ ወገን ጦር ዘላህ ላይ ፊት ለፊት በተያየ ጊዜ በየሥፍራው ሆኖ በቀኝ በግራ በማህል የሚዋጋው ወታደ[illegible]ተደራጀ ተሰለፈ ። ወዚር አዶሌ ጓደኞቹን አውራይ አህመድ ዲንን ፣ አህመድ ጐይታን ፣ ፋራ-ቃሃም አሊን ፣ ፋራቃሃም ሳቱን ይዞ በማህል የጋንዝ ገዥ አብድ ኢን ናስር ከነሰዉ በግራ ፣ አባስ (ወደፊት ወዚር የተባለው) ና ከራድ ኡስማን በቀኝ አብሳማ ኑርና ሰብርዲን ፣ ኤሚር አቡበከር . . . . . . ግንባር ቀደም ሆነው ተሰለፉ ። የእስላሞቹም የጦር አለቆች ስለ ቅዱስ ጦርነት መሞት ጥሩ አሟሟት መሆኑን ከዚህ ዓለም ተለይቶ ወደ ሰማይ መሄድና መንግሥተ ሰማያት ማግኘት ዋና ዕድል መሆኑን የዚህንም ዓለም ኑሮ የሚያስንቀውን እያነሡ እርስ በርሳቸው ንግግር አደረጉና ለሞት ወይም ለአሸናፊነት ተዘጋጁ ።

እስላሞቹ እንደዚህ ተሰልፈው ወደርሱ ሲራመዱ አዝማች አዳሉ የባሌ ጌታ የእግረኛውን ጋሻና ጦር የያዘውን ወታደሩን ከፈረሰኛው ፊት አስቀድሞ አሰለፈና እፈረሱ ላይ ወጥቶ እንደብረት ሕንፃ ቆሞ የመካከለኛውን ሥፍራ ያዘ ። ሴቶቹንና ልጆቹንም ልኮ አስመጣና « ዛሬ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነገር ሥራ የምንሠራበት ታላቅ የተከበረ ቀን ነውና የክት ልብሶቻችሁን ልበሱ ፣ ጌጣችሁንም አጊጡ» ብሎ አዘዛቸውና እኋላው አደረጋቸው ። ሌሎቹም ሹማምንት እርሱ እንዳዘዘው የርሱን ምሳሌ እየተከተሉ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እኋላቸው አድርገው ተሰለፉ ።

የሁለቱ ወገን ጦር በዚህ ዓይነት ከተቀራረበ በኋላ ከእስላሞቹ ውስጥ አደቅ የተባለው ሩጫ ዠምሮ ጦርነቱን ሲዠምር እስላሞቹ ሁሉ በቆረጠ የእስላም መንፈስ ተከታትለው ሲሮጡ ከክርስቲያኖቹም ወገን እንደዚሁ ሆነና ትልቅ የበረታ

ውጊያ ተዠመረ ፤ ዥግና ከዥግና ጋር ተጋጥሞ ይባባል ዠመር ። አዝማች አዳሉ ተወርውሮ እስላሞቹ መካከል ገባ ። ይኸን የመሰለ ጽኑ አስፈሪ ጦርነት ከቶ አልተደረገም ። የሁለቱም ጦር ተደበላለቀ ፡ እስላሞቹ የእግዚአብሔርን አንድነትና ታላቅነት እያነሡ ይጮሁ ዠመር ። በዚያን ጊዜ ፋራቃሃም አሊ ወደ አዝማች አዳሉ ሄዶ መታና ሁለቱም ከፈረሳቸው ላይ ወድቀው ሲተናነቁ እስላሙ ጩቤውን አውጥቶ የጠላቱን አንገት ቆረጠው ። እርሱ ሲወድቅ ክርስቲያኖቹ ፊታቸውን አዙረው መሸሽ ዠመሩ ። እስላሞቹም እየተከታተሉ ይፈጁዋቸው ዠመር ። እንኳን ወንዶቹ ሴቶቹም ሳይቀር በዚህ በባሌ ጦርነት እስላሞቹ በፈረስ ጠላትን ሲያባርሩ የእስላሞቹ ሴቶች በበቅሎ እየተከታተሉ እኔ ፩ የክርስቲያን ሴት እኔ ፪ ማረክሁ እየተባባሉ ተመለሱ ።

በዚህ ቀን ጦርነት በሺ የሚቆጠሩ የክርስቲያን አለቆች ሞቱ ። ከነዚሁ ውስጥ በጣም የታወቁት ፡-

፩ኛ. ይስሐቅ አብሣማ ኑር የገደለው ።
፪ኛ. አቢብ የጋቱር (ቀጡራ ?) ገዥ ሰይጣን ዥግና የወናግ ዥን ልጅ ሲሙ የገደለው ።
፫ኛ. ሲሙ የሻርቃህ ገዥ ገራድ አህመዱሽ የገደለው ።
፬ኛ. ጋፋኒ በቅርብ ከሰለሙት ውስጥ የገደለው ።
፭ኛ. ዘመንክር የአዝማች አዳሉ ልጅ ታማክ አቡን የገደለው ።
፮ኛ. መጀን ከሲሙ ጋር በቅርብ ቀን የሰለመው ሰበሩ የገደለው ። በድምሩ የሞቱት ታላላቅ ሹማምንት ቍጥራቸው ፩፻ ይደርሳል ።
፩ኛ. አዛዥ ዛኪራህ (ዘኪሮስ ?) ከንጉሡ ቤተሰብነት ያለው ።
፪ኛ. ከሐዲው ናክድያህ (ጥንት እስላም የነበረ ማለት ነው) ።
፫ኛ. ጊዮርጊስ የዳህረጐት ልጅ ፈራቃሃም አዳል የማረከው ።
፬ኛ. ካረጅ ማንሱር የማረከው ። የምርኮኞቹ ቍጥር እስከ ፪፻ ይደርሳል ። የሞተው የእግረኛና የፈረሰኛ ቍጥር እስከ ሦስት ሺ ይደርሳል ። የጦርነቱ ሥፍራ በሰው ሬሣ ተሸፍኖ ነበር ። ደምም እንደ ወንዝ ውኃ ፈሰሰ ። ፈረሶች ሴቶች ልጆች ድንኳንና ሀብት ሁሉ በእስላሞቹ እጅ ወደቁ ። ከእስላሞቹ ወገን ለሰማዕትነት የተመደቡት ባሊ ኑርና አህ አዋሚህ ብቻ ሞቱ (1) ።

## ምዕራፍ ፸፫
## ስለ አዝማች አዳሉ (አዳል ሰገድ)

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ከማይጨው ጦርነት በኋላ ከታወቁት ታላላቅ መኳንንት ውስጥ እንደነቢትወደድ መኰንን ደምሰው ያሉት በጦር ሜዳ ሲወድቁ እንደነ ደጃዝማች

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 367 - 386

ይገዙ በሀብቴ ያሉት ወደ ጠላት ገብቶ መጫሪያ ከመሆን ስደትን ሲመርጡ ከነዚያም ውስጥ አብዛኞቹ በጥንቃቄ ራስን ከመጠበቅ የተነሣ ወይም በዕድል በጦር ሜዳ ከመሞት የዳኑት አርበኝነትም መሰደድም በየምክንያቱ ያልሆነላቸው ብዙ መኳንንት ወደ ኢጣልያ ገብተው መኖርን ወደ መምረጥ እንዳዘነበሉ የታወቀ ነው ። የኢጣልያና የግራኝ ወረራ ይኸን በመሳሰለ ረገድ በብዙ ይመሳሰላል ። ጠባይ ተግባርን ሲመራ በየቀኑ በየዘመኑ በሰው ልጅ የሐሣርና የመከራ ዘመን ሲገለጥ ይኖራል ።

በማይጨው ጦርነት ዋዜማ ኃይለ ማርያም ማሞ ፣ በላይ ዘለቀ ፣ አሞራው ውብነህ ገረሱ ፣ ዱቄ በቀለ ወያ እንዚህን የመሳሰሉት ሁሉ በሕዝብ ዘንድ አይታወቁም ነበር ። ባላምባራስ አበበ አረጋይ የፖሊስ ሹም ብላታ ታከለ የማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር በመሆናቸው በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ ካልሆነ በቀር ከዚያ ውጭ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እምብዛም አይታወቁም ነበር ። ሌሎች የሚታወቁ ራሶችና ደጃዝማቾች ብዙዎች ነበሩ ። አገሪቱ ከተወረረች በኋላ በአርበኝነት እነዚህ ቀድሞ ታናሽ የነበሩት ሁሉ ራሳቸውን ምን ያህል ድረስ እንዳሳወቁ የምናውቀው ስለሆነ እነሆ ከነዚያ ከትልልቆቹ የበለጠ የታሪክ ሥፍራ ይዘዋል ።

እንደ ኤው. ቍጥር ፲፱፻፴፰ - ፵ ዓ. ም. በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ በፈረንሳይ ሕዝብና የጦር ሠራዊት መካከል [illegible]ወቁት የጦር አለቆች ማሬሻል ፔተ ገኔራል ዌጋን ገኔራል ጋሜለና እነዚህን የመሳሰሉ ነበሩ ። በዚህ ጊዜ ኮሎኔል በመጨረሻ ብሪጋዲዬር ገኔራል የተባለው ሻርል ደጎል የነዚያን ያህል ቀርቶ የነርሱን ሩቡን ያህል አይታወቅም ነበር ። ከነዚያ ውስጥ ግማሹ ሲሞት አብዛኛው ወደ አሸናፊው ወደ ጀርመን መንግሥት እየገባ አብሮ በመሥራት መጫሪያ ሲሆን ደጎል እምቢ ብሎ "ፈረንሳይ ባንድ የጦር ግንባር ተሸንፋለች እንጂ ፈጽማ ድል አልተመታችም ስለዚህ ትግላችንን እንቀጥላለን" የሚል ድምጽ እ. አው. ቍ ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፵ ዓ. ም. ከሎንዶን የራዲዮ ጣቢያ ባሰማ ጊዜ ስላገሩ መከላከል ያማረው ሁሉ በርሱ ዙሪያ ተሰብስቦ በመጨረሻ ያገሩን ነፃነት ለማቋቋም ቻለ ። ስለዚህ የአንዱ የርሱ ስም ዝናው የበላዮቹ የነበሩትን ስም ሁሉ በሕይወቱም በሞቱም ዘመን እንደሸፈነው ቀረ ።

በዚሁ ዓይነት በ፲፰፻፲፱ - ፳፱ ዓ. ም. ወይም በዋዜማው ባለፈው ምዕራፍ ተዋግቶ ሕይወቱን ላገሩ ሲሠዋ ያነበብነው አዝማች አዳሉ በሕዝብና በጦር አለቆች ዘንድ የታወቀ አይመስልም ። የታወቁትን ታላላቆቹን ራስ ወሰን ሰገድን ፣ ራስ እስላም ሰገድን ራስ ነቢያትን ፣ ራስ ደጋልሃንን ቢትወደድ ሠርጼንና በነርሱ ደረጃ ያሉትን በየምዕራፉ ተዋግተው የሞቱትንም ከንጉሡ ጋር ወደ ቤጌምድር የሄዱትን ወይም ወደ ግራኝ እየገቡ የሰለሙትን አንብበናል ። እርሱ ግን ካለመታወቁ የተነሣ ያገራችን አጭሩ የግዕዙ ታሪክ የሌሎቹን የታላላቆቹን ስም ሲያወሳ እርሱን በፍጹም ዘሎታል ።

የዝግንነቱ ሁኔታ በዝርዝር ተጽፎ ቢሆን በመጨረሻ ባደረገው ጦርነት አዶ

ሴን ቀጥሎ ግራኝን በማሸነፍ ቀንቶት ቢሆን ዝናው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍ ተኛውን ሥፍራ በያዘ ነበር ። እንደ እውነቱ ተሸንፎ መሞቱም የበለጠ ሊያገነው እንጂ ያነሰ ሊሆን አይገባም ።

በ፲፰፻፶፫ ዓ. ም. ላይ ራስ ወሰን ሰገድ ለክርስቲያኑ ጦር አለኝታና ተስፋ እን ደነበረ ከርሱ ሞት በኋላ ግን ግራኝ አህመድ ለደቡቡ ክፍል አዶሌን ጠባቂ አድርጎ ንጉሡን ለማባረር ወደ ዋስል ለመሄድ እንደደፈረ ፤ የራስ ወሰን ሰገድ ሞት ለክርስ ቲያኖቹ ተስፋ አስቆራጭ ለእስላሞቹ ታላቅ ደስታ እንደፈጠረ ፤ ወሰን ሰገድ የሞተ ጊዜ የምሥራቹን ለሡልጣን ኡመር ዲን ንገሩ ብሎ ግራኝ ወደ ሐረር መልክ ተኛ ልኮ እንደነበረ አንብበናል ።

አሁን ደግሞ ባመቱ ባለፈው ሰሙን የጠቀስነው ዝግናው አዳሉ በባሌ እንደ ርሱ ለሞት የቆረጡትን ሹማምንት ሰብስቦ በቊጥርም በድርጅትም በመሣሪያ ጥራ ትም ከርሱ የሚበልጡትን በወዚር አዶሌ የሚመሩትን ሠራዊት እንደምን ገጥሞ ከጓደኞቹና ዘመንክር ከሚባለው ከገዛ ልጁ ጋር ሕይወቱን ከሠዋ በኋላ እስላሞቹ በፊት ያላደረጉትን ባገሪቱ ላይ ለመቀመጥ ተዘናንተው ቤተሰብና ሚስቶቻቸውን ከየአገራቸው ከሐረርጌ ከአዳል ሲያስመጡ እናያለን ። ቀድሞ ከወሰን ሰገድ ሞት በኋላ እንዳደረገው አሁን ደግሞ ከአዳሉ ሞት በኋላ የደቡቡ አገዛዝ እንደተከናወነ በመቁጠር ግራኝ እምና የገመረውን የወረራና ንጉሡን የማሳደድ ሥራውን ለመ ቀጠል ፪ኛ ወደ ሰሜን ይሄዳል ።

ዝግንነቱ ያስደንቃል እንጂ የአዝማች አዳሉ ያሁኑ መሸነፍና መሞት ለማንም ሊገርም አይችልም ። የዘመኑን የጦር መሣሪያ የያዙ ዓረቦችና ቱርኮች ያሉበት በሰይፍ አመታትና አመካከት የሰለጠኑት የጦር አለቆቹ እነ አቡበክር እን አብሳማ ኑር ያሉበትን የደረጀና ትጥቁ ያማረውን ሠራዊት እንደምን ሊያሸንፍ ይችላል ። በዚህ ላይ ከራሱ ጦር ከዳተኛው ሰበሩ አሳቡን መላውን እንደያዘ ከጠ ሩም ከፍሎ ከጠላቶቹ ጋር ተሰልፎበታል ። በዚህ ዓመት ለግራኝ የገባው የወጅና የዝቋላ ዙሪያ ሕዝብ በቅርብ የገባው የሐድያ ሕዝብ በግድም በውድም ዘምቶበ ታል ።

ስለዚህ አዳሉ "ዛሬ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነገር ሥራ የምንሠራበት ታላቅ የተከበረ ቀን ነውና የክት ልብሳችሁን ለብሳችሁ ተዋጉ" ብሎ ካዘዘ በኋላ ጀብዱ ውን ሊደብቅበት ያልቻለው የዓረቡ ጸሐፊ "እፈረሱ ላይ ወጥቶ እንደ ሕንፃ ቆሞ የመካከለኛውን ሥፍራ ያዘ" እልፍ ብሎ ደግሞ "አዝማች አዳሉ ተወርውሮ እስላ ሞቹ መካከል ገባ" ብሎ እያገነነ መዝመሪያ አላህ መጀን ከሚባለው ጋር ብቻ ለብቻ ተጋጥሞ ገድሎ ቀጥሎ በተደረገው ጦርነት ከፈራቃሃም አሊ ጋር ተጋጥሞ በትንንቅ በሚዋጋበት ጊዜ ሁለቱም ውድቀው ፈራቃሃም ጩቤውን መዞ የአዳሉን አንገት ቆርጦ መግደሉን ጽፎታል ።

ይኸን የመሰለ ጀብዱ የሞላበትን የአዳሉንና የልጁን የዘመንክርን የጓደኞቹን የይስሐቅን የአቢብን አሚሟት በጠቅላላው ፳፪ ሹማምንት የሞቱበትን ፱፻ የተማ ረኩበትን ሦስት ሺ ወታደር ያለቀበትን የጦርነት ታሪክ የኛ ታሪክ ነገሥት ሳያነ

ሣው ማለፉ ይገርማል ። እንኳን ዝርዝሩን ታሪክ ለነራስ ወሰን ሰገድ ፥ ለነራስ እስ ላም ሰገድ እንዳደረገው ባንድ ወይም በ፱ መስመር ስሙን እንደተለመደ በጨረ ፍታ እንኳን ጠቅሶት አላለፈም ።

የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊ "ጸሐፌ ትእዛዝ ወይም በዓለ መጽሐፍ" የሚባለው ይኸ ሁሉ ውጊያ ሲደረግ እርሱ የግራኝ ጦር ባልደረሰበት በቤጌምድር ወይም በላስታ አገር ባንድ ገዳም ተቀምጦ ይሆናል ። ወይም ከንጉሡ ጋር እየተጓዘ አዳሉ በዚህ በባሌ ያደረገውን ውጊያ ፈጽሞ አልተገነዘበው ይሆናል ። ወይስ የዘመኑ ጸሐፊ ለማዕርጉም ለኑሮውም የንጉሡን እጅ አይቶ አዳሪ ስለሆነ ንጉሡ ከሸሹ በኋላ ሌላው የጦር መኰንን ከኋላ ቀርቶ የፈጸመውን አስደናቂ ተጋድሎ በታሪክ ጽሑፍ አስፍሮ ማቆየት የንጉሡንና ከርሳቸው ጋር ያሉትን የታላላቅ መኳንንት የተዋጊ ነት ክብር ይቀንሣል ወይፈትም የሚነግሠውን ቅር ያሰኛል ብሎ በአገልጋይነቱ አስቦ ትቶት ይሆን ? ያለዚያ የጦርነቱ ሁኔታ በቸልታ የሚታለፍ ነው እንዳይባል ዓረብ ፋቂህ ይኸን የመሰለ ጽኑ ጦርነት ከቶ አልተደረገም ሲል በራሱ አስተያየት ከዚህ በፊት ከተደረገው ሁሉ ውጊያ አብልጦታል ማለት ነው ።

መቼም በአሁኑ ሰዓት በቅርብም በሩቅም ያለው ጸሐፊ ባገሪቱ ላይ ሳይታሰብ የወረደውን ይኸን የጦርነትና የእልቂት የቃጠሎ የዘረፋ መዓት በልቡ እያሰላሰለ ነፍሱን የሚያድንበትን ያስባል እንጂ ተግባሬ ነው ወይም ለኋላ ትውልድ ይጠቅ ማል ብሎ በዚያን ሰዓት ታሪኩን በጽሑፍ ላይ ላስፍረው የሚል ጸሐፊ የሚገኝ አይ መስለኝም ። ያም ባጫጭሩ በግዕዝ ተጽፎ ያነበብነው የጦርነቱ ጊዜ አልፎ በነሠ ርፀ ድንግል ወይም በነሱስንዮስ ጊዜ ወሬ እየተጠየቀ የተጻፈ ነው ። የአይፈርሱን ጦርነት ከተረከበት ላይ ባጫጭሩ ታሪኩን በግዕዝ የጻፈው "የዚህ አገር ሰዎች እንደነገሩን ግራኝ በየካቲት ፲፪ ቀን ደርሶ በአይፈርስ ተዋጋ" ስለአለ የጻፈው በኋላ በወሬ ጥየቃ እንጂ በሥፍራው እንዳልነበረ ያስረዳል (1) ።

ከአዝማች አዳሉ ጋር ተዋግቶ በአብሳማ ኑር እጅ የሞተውን ይስሐቅን ታሪኩ እንዳነሣው እንብበናል ። ይህ ይስሐቅ ከዚህ በፊት ከነቢትወደድ ሠርጼ ጋር ሆኖ የአምባ ግሼንን ጦርነት የተካፈለው ይሆን ። የኛ ጽሑፍ ደገልሃን የግራ አዛዥ በነ በረበት ሰዓት የቀኝ አዛዥ ይስሐቅ ነበር የሚለው አለ (2) ። እርሱ ይሆን ወይስ ቀኝ አዛዡ ይስሐቅ በአይፈርስ ጦርነት ሞቶ አሁን ከአዳሉ ጋር የሞተው ሌላ ይስ ሐቅ ይሆን አይታወቅም ።

ዓረብ ፋቂህ በቀድሞ ጓደኛውና በከዳተኛው ወገኑ በሲሙ (ስምዖን) እጅ የሞ ተውን አቢብ የሚባለውን የጋተር (ቀጡራ ?) ገዥ ነገሩን ሳይዘረዝር ሰይጣን ዝግና ይለዋል ። ምናልባት አድብቶ ሲመቸው እያጠቃ ሳይመቸው እየሸሸ ለጠላት የማ ይመች የጦር ዘዴ አዋቂ የጦር አለቃ ይሆናል ።

አዝማች አዳሉ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የግራኝ ጦር በደቡብ በምሥራ

(1) ወበጽሐ እመ፲ወ፪ ለየካቲት በከመ ነገሩነ ሰብአ ውእቱ ብሔር መገብረ ጸብአ በአይፈርስ . . . . .

(2) Liber Axum Conti-Rossini 37.

ብና በምሥራቅ እየተከፋፈለ አውራጃውን ሁሉ ይዞ ሕዝቡን እያሰለመ በሚያስገ ብርበት ጊዜ እርዳታ ከዚህ ቦታ ይደርስልኛል ብሎ ተስፋ በማያደርግበት ወቅት ለውጊያ ተዘጋጅቶ መቅረቡ በእጠገቡ ያሉትን ስለአገርና ስለ ሃይማኖት መሞት እንደሚገባ ባገር ፍቅር ልባቸውን ቀስቅሶ እርሱ እንደ ሕንፃ ቊጥሩ ከበረከተ የጠ ላት ሠራዊት ፊት ተደቅኖ ከዚያም ተወርውሮ ከጠላት መካከል ገብቶ እላህ መገ ንን ገድሎ በተራው በፈራቃሃም እጅ ሲሞት የነበረው ተስፋ አንድ ብቻ ነው ይኸ ውም በዚህ ዓይነት ዠግንነት ተዋግቼና አዋግቼ ብሞት ወገኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ስሜን በታሪክ እያነበበ ያነሣዋል ነው ። የአሁንም የወ ደፊትም ትውልድ ምኞቱን በመፈጸም ይኸን ዠግና ማወቅና ማድነቅ አለበት ። ለዚሁ ዠግንነቱ መታሰቢያ ይሆነው ዘንድ ሐውልት ማቆሙ እንኳን ቢቀር በባሌ ከተማ ማህል የሚገኘው አውራ ጐዳና የአዝማች አዳል ሰገድ አውራ ጐዳና ተብሎ መሰየም የሰማዕትነት ዋጋውን እንደ መክፈል ይቆጠራል ።

የዠግንነቱን ታሪክ ወገኖቹ በዝንጋታ አልፈውት ፬፻ ዓመት ሙሉ በኢትዮ ጵያ ሕዝብ ዘንድ ተደብቆ ሲኖር ከጠላቱ ወገን የሆነው ዓረብ ፋቂህ በዓረብኛ ጽፎ ት ሲኖር ዓረብኛውን ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ድካም ያደረጉት ሬኔ ባሴት ወደ ፈረንሳዊ ስለተረጐሙት ከዚያም ዛሬ እኛ ወደ አማርኛ ልንተረጉመው ስለቻልን ከኛ የበለጠ ሁለቱ የውጭ አገር ሰዎች ከሁለቱም የታሪኩ መሥራች ዓረብ ፋቂህ ሊመሰገኙ ይገባዋል ።

## ምዕራፍ ፸፩

## አዝማች አዳሉ የተዋጋ ለት በተማረኩት ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ፍርድ የአዝማች አዳሉ ባለቤት መጥፎ ዕድል ።

አሸናፊው ወዚር አዶሌ ከድሉ በኋላ በሚያምረው በአዝማች አዳሉ ድንኳን ውስጥ ተቀምጦ የተማረከውን ሴቱንም ወንዱንም ሰብስቦ በባሌ ሳይዋጋ ተርፎ የተቀ መጠ የክርስቲያን ጦር እንዳለ ጠይቆ አምን የቃግማው (ቃጅማ ?) አይዳቢስ የደ ዋሮ ሹም በድሉ ሌሎች አምስት የሚሆኑ ሹማምንት አሉ እነሱም ተሰብስበው የሚገኙት በቃግማ በአይዳቢስ ቤት መሆኑን ያው ከዳተኛው ሲሙ እንደመለሰ በዚያን ጊዜ አዶሌ ፃ ምርጥ ፈረሰኛ ሰጥቶ አገርህ ስለሆነ በል አንተው ራስህ ሂደህ የሸሹትንም እያባረርህ ውጋ ብሎ እንዳዘዘው ዓረብ ፋቂህ ያረጋግጣል ። ከዚህም እያይዞ ሲሙ ወታደሮቹን ይዞ ወደ ቃግማ ሄዶ የክርስቲያኖቹን ሹማምንት በጫካ እንደትደበቁ አግኝቶ አታሎ በተንኮል እንደያዛቸው ፡ የፋኑኤልን ወንድም ድል ሰበር የሚባለውን እንደገደለውና ከዚያ ምርኮውን ይዞ ወደ አዶሌ መመለሱን ባንድ ወገን ደግሞ በግራኝ አህመድ ፈቃድ ደዋሮን የተሾመው ገራድ ጎሹ ወዚር አዶሌ ወደ ባሌ ከአዝማች አዳሉ ጋር ሊዋጋ ሲሄድ ከደዋሮ ወደ ባሌ ዘልቀህ የደረን በር ይዘህ እየተጠባበቅህ ከባሌ የክርስቲያን ጦር ሲሸሽ ጠብቅ ተብሎ አንድ እከ

ፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ ሲጠባበቅ ሐጋ የሚባለው የክርስቲያን መኰንን ከነሰዎቹ በርሱ በኩል ሲመጣ አይቶት ወደርሱ እስኪጠጋ ድረስ ዝም ብሎ በኋላ በድንገት ደርሶ አደጋ እንደጣለባቸው እነርሱም ደክመው ኖሮ አትውጉን ብለው ቢጮሁ በሉ ደግ ነው መሣሪያችሁን ጣሉ ብሎ አስጥሎ ከማረካቸው በኋላ ሁሉንም አንገታቸውን እያስቆረጠ እንዳሳረዳቸው በነዚህም ውስጥ የአዝማች አዳሉ ልጅ እንደነበረ ከታረዱት ውስጥ ፋሬስ የሚባለው ብቻ ክርስቲያን አልሃማይ ሶልጣን የሚባለው እንዳሰረው ሊያርደው ጠጋ ሲል ጩቤውን አውጥቶ ጉሮሮውን ወግቶ ገድሎ ሌሎች እስላሞች ሳያዩት እንደአመለጠ ዓረብ ፋቂህ ይገልጻል (1) ።

ሐጋ የሚባለው የክርስቲያን ሹም ከዚህ በፊት እሰልማለሁ ብሎ ከግራኝ ዘንድ የተላከለትን ሰው ገድሎ ያናደደ ሰው ስለነበረ ገራድ ጎሹ ግራኝን ደስ ለማሰኘት ብሎ የሐጋን ቊንቅላት ቆርጦ በእንጨት ሰክቶ ልኮለት ስለነበረ ግራኝ አህመድ በዚህ በሰውዬ አማካይነት የአዝማች አዳሉን ሞትና የጦሩን መሸነፍ ስለሰማ ወደ ውጭ ወጥቶ ነጋሪት እያስመታ ከተሰበሰበው ሕዝብ ጋር ደስታውን ተካፈለ ። የዚህንም ወሬና የሐጋን ቊንቅላት ላመጡት ሰዎች የወርቅ አምባርና የልብስ ሽልማት ሰጣቸው (2) ።

በበኩሉ ወዚር አዶሌ የባሌን አገር እያላደሎ ከያዘ በኋላ የአዝማች አዳሉን ሞት በደብዳቤ ጽፎ የላከው የጎሹ መላከተኛ ኢብራሂም በደረሰ በሁለተኛው ቀን ደዋሮ ወደ ግራኝ አህመድ ዘንድ ደርሶ ደብዳቤውን አስረከበ ። ምነው እስካሁን ቆየህ ብሎ ቢጠይቀው የዋቢ ወንዝ ሞልቶብኝ ነው አለ ። በደብዳቤው ላይ አዶሌ የተማረኩትን እስረኞች ሴቶቹንና ልጆቹን ፈረሶቹን ምን ላድርጋቸው ብሎ ጠይቆ ነበርና ስለ ሁሉም ጠቅላላ ትእዛዝ ግራኝ እንደዚህ ሲል መልሶ ላከበት ፤

«፩ኛ. ከምርኮው ሀብት አምስተኛውን ዕጣ (⅕) አውጥተህ የቀረውን ለተዋጋው ወታደር አከፋፍለው ፤
፪ኛ. የአዝማች አዳሉን ሚስት ለራስህ ዕቁባት አድርጋት ፤
፫ኛ. የተማረኩትን ሹማምንት እሺ ብለው የሚሰልሙትን እዚያው ካንተ ጋር አስቀምጣቸው እምቢ ያሉትን ግደላቸው ።
፬ኛ. ከሓዲውን ናክዲያሀን (3) በዘላሀ በር ላይ አሳንቀህ ስቀለው ፤
፭ኛ. ካርጅን ፤ ዞኪራሀን እጂ ቆራጣውን ፤ ጊዮርጊስን የዳረጐትን (ድኅር ጐይታ) ልጅ አራት ፈረስ ጨምረህ (ባራት ፈረሰኛ አሳጅበህ ?) ወደኔ ላካቸው ፤
፮ኛ. ለአብድ ኢን ናስርና ለሐድያው ባላባት ከምርኮው ከፈረሶችም ከሹማምንት ሚስትም ድርሻቸውን እየሰጠህ በየአገራቸው አሰናብታቸው ፤
፯ኛ. እስላሞችን ሳይከዳ በታማኝነት ለተዋጋው ለሲሙ መጨበሚው በጽ ወቅት ጥሩ ወርቅ የተለበደውን ሰይፍ ላክለት» ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 385 - 387
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 388
(3) ከግራኝ ወደ ክርስቲያኖች ዞሮ ሲዋጋ የኖረ ነው ዓረብ ፋቂህ ገጽ 50

አዶሊ እንደታዘዘው አድርጎ የተጠየቁትን የክርስቲያን ሹማምንት ወደ
ግራኝ ልኮ በደረሱ ጊዜ ግራኝ ሀብታቸውን ከወሰደ በኋላ ሁሉንም አንገታቸውን
እያስቆረጠ አስገደላቸው ጋርጅ የሚባለው ቀድሞ እስላም የነበረ ሲገደል ሲል
ባጠገቡ ያሉት ሹማምንት ከሕፃንነቱ ዠምሮ አንተ ቤት ነውና ያደገው ማረው
ብለው ለምነው አስማሩት (1) ።

በጠቅላላው ሲዋጋ በተማረከውና ሲዋጋ በሞተው ቤተሰብ ላይ የግራኝ ፍርድ
ይኸን የመሰለ ነው ። ሴቱንም እንደ ዕቃና እንደ ከብት እሽናፊዎቹ ይከፋፈሏቸ
ዋል ። መከረኛዪቱ የዠግናው የአዳሉ ባለቤት በጦር ሜዳ ባሉዋንና ልጅዋን ያጣ
ችው ቋንቋውን ለማታውቀው ሃይማኖቱ ለማይመስላት ለወዚር አዶሌ ዕቁባት
ስትሆን ምን ይሰማት ይሆን ፣ ጠባይዋ ተናዳጅ ይሁን ግዴለሽ ትሁን አናውቅም ።
ይሁን እንጂ ከዚህ ሁሉ አደጋ መካከል ነዋሪ ሃይማኖቷን ለውጣ የባሏ ጠላት ዕቁ
ባት ሲያደርጋት ያስደስታታል ተብሎ አይታሰብም ። የልቧን ሽብርና ንዴት መጠ
ኑን በፍጹም አናውቀውም የምትወደውን ባሏን አጥታ የማትወደውን ለማግባት
ከተገደደችው ሚስቱ በጦር ሜዳ በጀግንነት የሞተው የባሏ የአዝማች አዳሉ ዕድል
በጣም የተሻለ ሳይሆን አይቀርም ።

የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ግራኝ በዚህ ዓይነት ሲያምስ የርሱ የሩቅ ደጋ
ፊው ታላቁ የቱርክ ሱልጣን ሶሊማን በዚሁ ጊዜ በአውሮፓ ግንባር ነምሳዎችን
ሰርቢያኖችን ሐንጋሪያኖችን እየወጋ የሚያስገብርበት ዘመን ነው ። ከዚያ በፊት
ትንሽ ቀደም ብሎ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ሁሉ ሲገብር ደሴትነቷና ምሽግ ተመችቷት
ለሱልጣኑ ሥልጣን ሳትንበረከክ የቆየችው የሮዶስ ደሴት በውስጧ መሽገው የተ
ቀመጡት የግሪክ የማልት የቬኔዚያ የፈረንሳዊ ፣ የጀርመን ፣ የእንግሊዝ ክርስቲያ
ኖች ከፍ ያለ የክርስቲያን ጕራ አበጅተው አውከው ይኖሩ ነበር ። የሱልጣኑ ጦር
እያለፈ ብዙ አገር ሲያስገብር ይቺ ደሴት በኃይሏ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ተከላክላ
መቆየቷ ስለነደደው እራሱ ሱልጣን ሶሊማን አዝማች ሆኖ ወደዚች ደሴት በመር
ከብ ብዙ ጦር አስመጥቶ ከበባት ። ከባቢዎቹም ወደ ውስጥ ድረስ እየዘለቁ በሁለ
ቱም መካከል ከፍ ያለ እልቂት ሲደረግ በውስጥ ያሉት ሴቱም መነኮሳቱም ቀሳው
ስቱም ከተዋጊው ወታደር ጋር ተደባልቀው እየተዋጉ ብዙዎቹ አለቁ ። በዚህ ጊዜ
አንድ የግሪክ ክርስቲያን ሴት አብሮአት የሚኖረው ወዳጇዋ የእንግሊዝ ካፒቴን
እፊቷ ተመትቶ ሲወድቅ አየችው ወዲያው ወደቤቷ ሮጣ ሄዳ ልጆቿን ስማ የመስ
ቀል ምልክት በላያቸው አማትባ ጠላት በዚህም በሚመጣውም ዓለም በናንተ ላይ
ሥልጣን አይኑረው ብላ በጩቤ ገድላ በደም የተበከለውን የወዳጇዋን ኮት ለብሳ
ሰይፉን እያውለበለበች ወደ ጦርነቱ ውስጥ ሄዳ ለመማታት ስትሞክር አንድ የቱ
ርክ ወታደር በጦር ወግቶ ገደላት (2) ።

በዚህ በግራኝ ዘመን ወንዱ ይኸን ያህል ሲተላለቅ ከሴቶች በኩል የተፈጸመ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 387 - 391

(2) Soliman le magnifique ገጽ 57

ውን መከላከል እናውቅም ። የአዳሉ ሚስትም የአሽናፊ ዕቁባት እንድትሆን ከተፈረደባት በኋላ ፍጻሜዋ አይታወቅም ። ሁሉ በየመልኩ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ የዚህ ዘመን የጦርነት ታሪክ ብዙ አድራጐት የተሸከመ መሆኑ አይጠረጠርም ። ዳሩ ግን እንኳን የሴቱ የወንዱም የተጻፈለት በልክ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ከአዝማች አዳሉ ውድቀት በኋላ የተማረኩትን ሹማምንትና ሴቶች ምን ላድርጋቸው ብሎ የበላዩን አዛዥ ግራኝን መጠየቁ ወዚር አዶሌ ምርኮኞቹን እንደማረክ አለመግደሉን ያስረዳል ። በፖለቲካው አመራርና በሕይወት ላይ ሥልጣን ያለው የበላዩ ግራኝ ሳያዝ ምርኮኛ መግደል አይቻልም ማለት ነው ። ግራኝም እሺ ብለው የሚሰልሙትን ካንተው ጋር አስቀምጣቸው እምቢ አንሰልምም ያሉትን ግደላቸው ሲል አገዳደሉ ውስታ አለው ማለት ነው ። ገራድ ጎሹ ግን ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው በድካም የሚሄዱትን በደፈጣ አግኝቶ ውጊያ ስልችቷቸው ወይም አቅም አንሷቸው ማርከን አትግደለን ሲሉት በሉ መሣሪያችሁን ጣሉ ብሎ ከአስጣለ በኋላ ማሳረዱ የመንፈሱን ወራዳነት ያሳያል ።

ይህ ጎሹ የተባለው እስካለፈው ዓመት ድረስ ካፄ ልብነ ድንግል ጋር ነበር ። በዋስል ጦርነት ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በጥቅምት ወር ግራኝ ድንገት ደርሶ አደጋ ጥሎ የተዋጋ ለት ከርሳቸው ሠፈር ሮጦ መጥቶ «እኔ እንደናንተው እስላም ነኝ ልጄ በሻራህ ከናንተ ጋር ነው» ብሎ ወደ ግራኝ መዞሩን አንባቢ ያስታውሰዋል ።

ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ከእንግዶቹ ይል[illegible]ርስቲያኖቹ ጋር አብረው የነበሩት እስላሞች ይጨክናሉ ማለት ነው ።

የዚህን የባሌን ጦርነትና አዝማች አዳሉ የሞተበትን ዓመት ዓረብ ፋቂህ ዓርብ በ፱፻፴፫ የሂጅራ ዓመትና ያመቱ ወር መጨረሻ ያለውን ሙሴ ረኔ ባሴት እንደ አው. ቀ. ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ሐምሌና ነሐሴ ወር መካከል አድርገውታል (1) ። በኛ ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ነው ፤ ወሩ ግን አንደኛው ያመት የመጨረሻው ወር ነሐሴ ይሆናል ። ወዚር አዶሌ የምሥራች ለመንገር የላከውን መላክተኛ ለምን እስካሁን ቆየህ ብሎ ግራኝ ሲጠይቀው የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሞልቶብኝ ነው ስላለ ክረምትነቱ የታወቀ ነው ። በዚህ ዓይነት አዝማች አዳሉ ተዋግቶ የሞተው ራስ ወሰን ሰገድ ተዋግቶ በሞተ ልክ ባመቱ መሆኑ ነው ።

## ምዕራፍ ፭፰

## የጋንዝና የወረባ ለግራኝ አህመድ መገዛት (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ከአዳሉ ሞት በኋላ በዚህ በደቡቡ ክፍል ያለውን የክርስቲያን ጦር በያለበት ተበታትኖ የተራረፈውን ለመልቀም ለግራኝ አህመድ በዚህ ጊዜ ፈጽሞ ቀላል ሆነ ። ይኸም የተረፈ ጦር ሹማምንቱ በወጅ እስላም ደሀር ፤ በወረባ አክሊል የሚባል

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 390

ከዓፄ ልብነ ድንግል ሹመት ሳያገኝ እንደዚሁ ሸፍቶ የተቀመጠ ፣ በጋንዝ አይከር የሚባሉ ናቸው ።

እስላም ደሀር ያፄ እስክንድር አማች የከም ደሀር ልጅ የወጅ ሹም መሆኑ ከዚህ በፊት አገሩ እንዳይዘረፍበት እርሱ ራሱን ወደኋላ አስቀርቶ ልጁን ወደ ግራኝ ከጭፍራ ጋር ልኮ አስልሞ በአገሩ በሰላም ለመቆየት ምኞት የነበረው መሆኑን በዚያም ጊዜ ግራኝ በቶሎ ጦር ሲልክበት እስቦ ሳለ በአጠገቡ ያሉት ልጁን ከላከል ንና ከገበረ ይበቃል እዚያው ይቀመጥ ብለው መክረው ለጊዜው ግራኝን እሺ እንዳ ሰኙት አንብበናል ። ግራኝም ለጊዜው እሺ ያለበት «የት ያመልጣል» በሚል ውስጠ ዛቻ ወደፊት የሚያደርገውን ሙሉ አገዛዝና አሁን ያገኘውን ግማሽ አገዛዝ በማመዛዘን መሆን አለበት ። አሁን ግን አስፈሪው አዳሉ ከሞተ በኋላ በግማሽ ታማኝነትና በአጠራጣሪ ሁኔታ የተቀመጠው የእስላም ደሀር ሁኔታ ለአሸናፊው ለግራኝ አህመድ ስለአላስደሰተው ወጅን በፍጹም ደምስሶ ለማስገበር ሲል አው ራይ አቡንን ጦር አሲዞ ላከው ። እስላም ደሀርም ተራራ ይዞ ለመከላከል ሲዘጋጅ ከላይም ከታችም ሆነው ስለወጉት ወታደሩ መሸሽ ዠመረ ። እስላሞቹም እየተከታ ተሉ ፈጁዋቸው ። እርሱም መጨረሻውን ተይዞ ተገደለ ። በዚህ ዓይነት የልጁም በቅድሚያ መስለም ፣ የርሱም በሩቁ እየገበረ መቀመጥ አላዳነውም ማለት ነው ። ከዚህ በኋላ ወጅ በሙሉ ከዳር እስከ ዳር ገበረ (1) ።

በበኩሉ ከዚህ በፊት ጋንዝን የተሾመው ከሐድያው ባላባት ጋር የተጋባው አብድ ኢን ናስር ከአዝማች አዳሉ ጦርነት በኋላ ከባሌ ከሐድያው ባላባት ጋር ሆነው ወደ ሐድያ ተመልሰው እንደደረሱ አይከር የሚባለውን ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ጦር አሲዘው ወደ ጋንዝ ልከውታል ማለትን ስለሰማ አብድ ኢን ናስር በቶሎ ወደርሱ ዘንድ ሄዶ ጦርነቱ እንደተዠመረ አይከር ብቻ በፈረሱ ላይ ወጥቶ ሲያመልጥ የቀረው የጋንዝ ሕዝብ አሜን ብሎ ተገዝቶ እንደሰለመ ዓረብ ፋቂህ ያረጋግጣል ።

ስለዚህ አሁን የቀረው ሀብታሙና ለምለሙ የወረባ አገር ነው ። እንደ ዓረብ ፋቂህ አነጋገር የወረባ አገር በዚሁ በወጅና በሐድያ በጉራጌ አጠገብ ነው ገበርጌና ሻጋራህ የሚባሉ ወረዳዎች በአጠገቡ ይገኛሉ ። የአገሩ ሀብታምነትና ፍሬያማ ነት የተደነቀ ነው ። በዚሁ ምክንያት የዚህኑ የወረባን ወረዳ መያዝ ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል በሰሙበት ቀን ጸጸታቸውን የገለጹ ጊዜ ሀብታምነቱን ገልጸ ዋል ። ይኸን ወረዳ የሱስንዮስ ዜና መዋዕል በብዙ ቦታ "ወረብ" እያለ ይጠቅሰ ዋል ። ባንድ ቦታ ላይ «ንጉሡ ከሲዲ ጋር ለመዋጋት ወደ ሐድያ ሲሄድ ጉደርን ሞልቶ አገኘው ። ከዚያ እንደገብጣን (የዛሬው አዲስ ዓለም አካባቢ) ደርሶ . . . . . ቀጥሎ ወረብ በደረሰ ጊዜ ጥቂት የጉራጌ ተወላጆች ተቀበሉት» ይልና በሌላ ላይ ደግሞ ባፄ ያዕቆብና ባፄ ሱስንዮስ ዘመን የጐንደር መንግሥት እንደራሴ የነበሩት ራስ ዘሥላሴ (ዘሶ በእጁ ነግሦ) የተባሉት አገራቸው በዚሁ በወረብ መሆኑን ያመለ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 391 - 392

ክታል ። ይህም አነጋገር ከዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ አልራቀም ። በብዙ ቦታ የወረብ ወሰኑ እስከ ዓባይ ወንዝ እንደሚደርስ ያረጋግጣል (1) ። በዛሬ ጊዜ በሐድያና በጉራጌ በወጅ አጠገብ ያለው ለምለሙ ሻሸመኔ ሲመስል በአነጋገሩ እስከ ዓባይ ወንዝ ይደርሳል ስላለ ይኸን ያህል መርዘሙ ስለሚያጠራጥር በጠቅላላው የዛሬው በቾና ሜታ መሆን አለበት ። ምናልባትም ያን ጊዜ ወረባ ታላቅ ወረዳ በመሆኑ ስፋቱ ወይም ቁመቱ ከጉራጌ አገር እስከ ዓባይ ወንዝ ይደርስ ይሆናል ። መቼም ከግራኝ ወረራ በፊት ተተክሎ የነበረውን ያገርና የወረዳ ስም ሁሉ ከጋሎች ወረራና ሥሪት በኋላ በጋልኛ ሥያሜ እየተለወጠ ስለተተካ በትክክል የቀድሞውንና ባዲስ በጋልኛ ሥያሜ በሙሉ የተተካውን ለማወቅ የረጅም ጊዜ ጥልቅ ጥናት ያስፈልጋል ። በዛሬው ጊዜ በሰልጢ ወረዳ አንድ ውርበራ የሚባለው ምክትል ወረዳ ከተማው ወራቢ ስለሚባል ግዕዝኛው ወረብ ዓረብኛው ወረባ ሲል የቆየው በጋሎቹ አጠራር ዛሬ ቅሪቱ ውርባራ ወይም ወራቢ ተብሎ እንደሆነ አይታወቅም ።

ዓረብ ፋቂህ በዚሁ በወረባ ቀድሞ ዓፄ እስክንድር (፲፬፻፸ - ፲፬፻፹፯ ዓ. ም.) ጥሩ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን የሰጡትን የበረከተ ወርቅ አምና ከቢር መሐመድ የሚባል የግራኝ ሹም ሲዘርፍ በተጉለቱ በተክለ ጊዮርጊስ የሚታዘዙት ክርስቲያኖች እንደገደሉት አመልክቷል ።

ከዚሁ አያይዞ በአሁኑ ሰዓት ባንድ ወገን ግራኝ አህመድ ያኪም የሚባለውን ወረባን ሄደህ አሳምን ብሎ ጦር ሰጥቶ እንደ[illegible]ው በዚሁ በወረባ አንድ አክሊል የሚባል ከንጉሡ ያልተሾመ ሽፍታ ስለነበረ ያኪም ሲሄድ በዚያ የሚገኙት ክርስቲያኖች ተሰብስበው አክሊልን መሪ አድርገው አንድ ሰዓት ያህል እንደተዋጉ በሺ የሚቆጠር ሰው ስለሞተባቸው አክሊል ብቻውን በፈረሱ ሸሽቶ ካመለጠና የእስላሙ ሹም ያኪም በለምለሟ አገር በወረባ ተደላድሎ ከተቀመጠ በኋላ ያገሩ ሕዝብ ግብር ቁረጥልን ብሎ መጠየቁን ለግራኝ ስለ አስታወቀ ግራኝ ባመት ፲፭ሺ ጭንት (ዳውላ ?) ስንዴ ፤ ፩ሺ ወቄት ወርቅ ፤ ፩ሺ ጉንዶ ማርና ቅቤ እንዲከፍሉ ስለወሰነ ባላገሩ ይኸንኑ ግብር እሺ ብሎ እንደተቀበለ ያወሳል (2) ።

በዚህ ሰዓት በአንኮት የሚገኙት ዓፄ ልብነ ድንግል የወረባን በእስላሞቹ መያዝ ሲሰሙ በጣም አዝነው ይቺ አገር ገነት ስለሆነች ያጣናት እንደሆነ ዘውዳችንም ኃይላችንም መጥፋቱ ነው ። ስለዚህ ሄደህ ተከላከል ብለው በፊት የዚሁ ወረዳ መምሹም ለነበረው ለራስ ነቢያት ነግረውት ነቢያት ጦር ይዞ ከአንኮት ወደ ወረባ መምጣቱን እንደመጣም እስላሞቹን ካገራችሁ ለማባረር ከንጉሡ ተልኬ መጥቻለሁና እርዱኝ ብሎ መላክተኛ ለየባላገሩ ቢያስለፍፍ ባላገሩ መላክተኛውን ሰድቦ እስላሞቹ ከእስፍሮ እንደመለሰውና መላክተኛው ለራስ ነቢያት ይኸንኑ ቢነግረው የባላገሩ ከእስላሞቹ ጋር መስማማት ገርሞት እንደተደነቀ ቀጥሎም ያኪም ጦር ይዞ ቢሄድበት

(1) የሉስንዮስ ዜና መዋዕል ምዕ. 15 ቍ. 10 ምዕ. 22 ቍ. 203 ምዕ. 34 ቍ. 5
(2) ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ማስታወሻ ገጽ 239

ሳይመክት ወደመጣበት እንደተመለሰ የዓረቡ ጸሐፊ ይገልጻል (1) ።

ስለዚህ በዚህ ዓይነት ግራኝ አህመድ በዚህ በደቡቡ ክፍል ከዚህ በፊት ወደ ቤተ አምሐራ ከመሄዱ በፊት ግራና ቀኙን በችኰላ እየወረረ ያለፈባቸውን አሁን ከቤተ አምሐራ ከተመለሰ ወዲህ በመዝናናት የእስላም ነክነት ባላቸው አውራጃ ዎች አንድ ጊዜ በጉራጌ አንድ ጊዜም በደዋሮ ተቀምጦ ግራና ቀኝ ጦሩን ብቻ እየላከ እነዚህን ሀብት የሞላባቸውን ወረዳዎች በጸጥታ አስገበረ ። ከመደላደሉና ካለመስጋቱም የተነሣ ለአስፈሪው ለአዝማች አዳሉ ጦርነት እንኳን እንደራሴውን አዶሊን ላከ እንጂ ራሱ አልዘመተም ።

ከዚህ በኋላ አገራቱን ለመግዛት እርግጠኝነት ስለተሰማው ከዚህ በፊት እንደ ሚያደርገው ወደ ሐረርጌ ሄዶ ተዘጋጅቶ ለወደፊቱ ጦርነት በመዘጋጀት ፈንታ ከዚሁ ከደቡቡ ክፍል በነበረው ላይ አዳዲስ የሚገባው ጦር በየጊዜው ስለበረከተ ለት የርሱንም የጓደኞቹንም ጓዝና ቤተሰብ ከሐረርጌ ለማስመጣት ወሰነ ።

ቤተሰቡንም ከአስመጣ በኋላ በፊቱ ያለው ምኞት ጦር ይዞ ከዚህ በፊት ሄዶ ወደተመለሰበት ወደ ሰሜን ፪ተኛ ዘምቶ ንጉሡን እየተከታተለ ለመውጋትና ያልደ ረሰባቸውን የላስታና የትግሬን የቤጌምድርንና የጐጃምን አውራጃዎች ለማስገበር ነው ። ይኸን አሳቡን ከዚያው ከታሪኩ ምንጭ ከዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ላይ እናን ብብ ።

«የወጅ የወረባ የፈጠጋር የደፋት አገሮችና በዙሪያውም የሚገኙት ሁሉ እንደ ገበሩለትና የሀበሻ አገር ሩቡ ወይም ሲሶው ከሥልጣኑ በታች መሆኑን ሲያውቅ ኤሚሮቹን የጦር ሹማምንቱን ወታደሩን ሁሉ እፊቱ ሰበሰበና እንደዚህ አላቸው ፤ "የሀበሻን ሀገር ድል ለማድረግ የፈቀደልኝ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ ይቺን አገር ድል አድርገን ከያዝን በኋላ ለቀን ወደ አገራችን መመለስ አይሆንምና እንግዲህ ወደ ሰዓዲን አገር (ሐረርጌ) እየላክን ሴቶቻችንንና ልጆቻችንን እያስመጣን እዚሁ አገር እንቀመጥ ። ለዚህ ጉዳይ እናንተስ ምን ምክር ትሰጣላችሁ ቢላቸው እስላ ሞቹ የማዘዙ ፈንታ ያንተ ነው እኛ ግን የመሰለህን ብታደርግ እንታዘዝሃለን ብለው መለሱለት ።

ስለዚህ ወዳገሩ ለሱልጣን ኡመር ዲንና ለወንድሙ ለመሐመድ ቤን ኢብራ ሂም "ይህ መላከተኛ ደብዳቤዬን ይዞ ወደ ናንተ ዘንድ እንደደረሰ ሴቶቻችንና ልጆ ቻችንን ላኩልን" የሚል ደብዳቤ ጽፎ ላከ ። በዚሁ ጊዜ ከሀበሻ አገር ያገኘውን የከ በረ ዕቃ ገጸ በረከት ወደ አዳል አገር ለሱልጣን ኡመር ዲንና ለሹማምንቱ ሁሉ ላከላቸው ። እያንዳንዱ እስላም እንደአቅሙ ለየቤተ ሰቡ ፳ም ፴ም ወቄት ወርቅና በቅሎ እየጨመረ ጓዙና ሚስቱ እንዲመጡለት መላከተኛውን ላከ ።

የይማም መላከተኛ አዳል አገር (ሐረርጌ) ደርሶ ደብዳቤውን ለሱልጣኑ አስረ ከበ ። ሱልጣኑም ወደ ባሎቻቸው ለሚሄዱት ሴቶች ሁሉ የይለፍ ወረቀት ሰጣ ቸው ። የይማም ሚስት ባቲያ ድል ወምበራና ግማሹ ሴት ወደ ሀበሻ አገር ለመም

(1) ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ማስታወሻ ገጽ 393 - 394

ጣት መዘጋጀት ሲዠምር ግማሹ አልሄድም ብሎ እምቢ ብሎ ነበር በኋላ ግን እስከ አይፈርስ ድረስ እየመጡ ከይማም ተገናኙ ።

ከዚህ ቀጥሎ ይማም ወደ ትግሬ ለመዝመት የጦር አለቆቹን ሁሉ ሰበሰበ ። ባሌ የነበረውንም ወዚር አዶሴን ልኮ አስመጣው ። ከዚህ በኋላ ለደዋሮ ኤሚር ሑሴንን ፡ ለሻርቃህ ገራድ ሴዲቅን ፡ ለደዋሮ ገራድ ጃሹን (ከኤሚር ሑሴን በታች ይሆናል) ። ለባሌ የወዚር አዶሴን ወንድም ኡመርን ትቶ ከአይፈርስ ወደ ወጅ ሄዶ ሙዝ ገቢያ እምትባል ከተማ ላይ ሰፈረ» (1) ።

## ምዕራፍ ፳፮

### ግራኝ ወደ ሰሜን ፪ኛ ከመዝመቱ በፊት የደቡብ ግዛቱን እያስፋፋ እንደያዘ ፤

ግራኝ አህመድ ወደ ሰሜን ሁለተኛ ከመዝመቱ በፊት የራሱን የጦር አለቆቹን ቤተሰቦች ካስመጣ ፡ ሹማምንቱን ሁሉ በተያዙት አውራጃዎች በደዋሮ ፡ በፈጠጋር ፡ በይፋት ፤ በባሌ ፡ በወጅ ፤ በጉራጌ ፤ በጋንገ እየደለደለ ከሾመ በኋላ የኢትዮጵያ ግዛት ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ ራሱ የደቡቡ ክፍል በሙሉ ስለአልተያዘ ከነዚህም ጋር በተለይ የራስ ወሰን ሰገድ የመጨረሻ ግዛት የነበረው ዳሞት ስለአልተያዘ ጉዞውን ወደ ሰሜን ከመዠመሩ በፊት እነዚህን ያልተያዙትን አውራጃዎች ለመያዝና ግዛቱን ከክርስቲያኖቹ አገዛዝ አጣርቶ እጅ ለማድረግ አሰበ ።

በዚህ ምክንያት እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ በግራኝ አህመድ ትእዛዝ ወዚር ሙጋሂድ ሱፍ ጋሞ ባሕር ጋሞ ወደሚባሉ አገሮች ሄደ ። እነዚህም አውራጃዎች የወላሞና የሲዳሞ አውራጃዎች ናቸው ። የሆነ ሆኖ ሙጋሂድ በነዚህ አገሮች ላይ ያገኘውን እየተዋጋ ሲገዛ አገሬው ምስለኔህን ላክልንና ግብር እንስጠው ብለው ላኩበት ። እርሱም ይኸን ሲሰማ እሺ ብሎ በጉብዝና በድፍረት የታወቀውን ሳሊህን ጦር ሰጥቶ ከመላክተኞቹ ጋር ላከው ፡ እነዚያም ወላሞ ከረግረጋማውና ከስንጥቁ ቦታ ሲደርሱ "እንግዲህ እኛ ግብሩን እስክንሰበስብ ድረስ እናንተ እዚህ ጠብቁን" ብለው ሄዱና ቆይተው ባላገሩን ይዘው መጥተው በመገበር ፈንታ ይወጉዋቸው ዠመር ። በዚህ ጊዜ እስላሞቹ ከፈረሶቻቸው ላይ ወጥተው እንዳይዋጉ የፈረሶቹ እግር ከማጡ ውስጥ እየገባ አላስሄድ ብሎ ባላገሮቹ እስላሞቹን ከአለቃቸው ከሳሊህ ጋር በሙሉ ፈጁዋቸው ።

ዋናው አለቃ ወዚር ሙጋሂድ የዚህን ወሬ ሰምቶ እነዚህን ባላገሮች ወግቼ የሳሊህን ደም ሳልበቀል ከዚህ አልሄድም ቢል በአጠገቡ ያሉት "ይህ አገር ለፈረስ የማይመች ስለሆነ በመከከሉም ክርስቲያኖቹ መመለሻ መንገዳችንን የዘጉብን እንደሆነ ተቆርጠን እንቀራለን" ብለው ቢለምኑት እምቢ ብሎ ፩ ወር እንደተጠ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 394 - 396

ባበተ በመካከሉ ስንቅም አልቆ መንገዱንም ክርስቲያኖቹ ዘግተውበት ሳለ አብድ ኢን ናስር የሚባለው የጋንዝ (ሚጫና የዛሬው አምቦ ዙሪያ ይመስላል) ገዥ የዚ ህን ወሬ ሰምቶ ሌትና ቀን ገሥግሦ በ፳ ቀን ውስጥ ደርሶ ከክርስቲያኖቹ ጋር ተዋ ግቶ በሩን አስለቅቆ ከነሞጋሂድ ለመገናኘት በደስታ ወደኋላቸው እንደተመለሱ የዓረቡ ጸሐፊ ያመለክታል (1) ።

በዚህ ጊዜ ግራኝ አህመድ በበኩሉ ፈጠጋር ሳለ የወዚር ሞጋሂድና የአብድ ኢን ናስር ወሬ ስለጠፋበት ሰግቶ ኖሮ ኤሚር ሻሙንና አብሳማኑርን ከአሉበት ተፈላልጋችሁ አምጡልኝ ብሎ አዟቸው እነዚህ ወደነዚያ እነዚያ ወደነዚህ ሲመጡ ከመንገድ ላይ ተገናኝተው ወደ ግራኝ መጥተው የደረሰውን ሁሉ ተረኩለት ።

ከዚህ በኋላ ከላይ የጠቀስነውን የዳሞትን ግዛት አስገብር ብሎ አብድኢን ናስ ርን እነሲዲ መሐመድንና ሌላም ብዙ ጦር ጨምሮ ወዚር አዶሌን ልኮት ሳለ በዳ ሞት የነበረው የክርስቲያኖቹ ሹም ደሀርጐት (ደሀር ጐይታ) የእስላሞቹን መም ጣት ሲሰማ የዳሞት ግዛት ወደሆነው ወደ ጋፋት እንደሄደ የጋፋት ሕዝብ ሃይማ ኖት የሌለው አረመኔ መሆኑን ፤ ደሀርጐት ሕዝቡ “ወደ አገራችን አትግባብን” እያለ ሲያወግዘው እምቢ ብሎ መግባቱንና ባላገሩ በጫካና በረግረጉ ሥፍራ ተደብቆ እንደወጋውና እርሱ ከጥቂት ሰዎቹ ጋር ብቻ ሲያመልጥ የቀረው ሕዝቡና ፲ ልጆቹ በጋፋት ባላገር ተገድለው ማለቃቸውን ይጽፋል ። እንደዚሁም እስላሞቹ ዳሞት ሲገቡ በለው ሰገድ የሚባለው ፴ ፈረሰኛ ይዞ የዚቤን (ጊቤ?) ወንዝ ተሻግሮ እናርያ ደርሶ አንዱን ዘሩ ባርያ የሆነ የዳሞት ተወላጅ እንዲያድነው ለምኖት እሺ ካለው በኋላ አዘንግቶ ከሠፈረበት በለው ሰገድን ከነጭፍራው ይዞ ወስዶ ለወዚር አዶሌ እንዳስረከበው እናሪያም የወርቅ አገር በመሆኑ በለው ሰገድን ባስረከበበት ቀን የእ ናሪያ ሕዝብ ከሌላው ገጸ በረከት በቀር ፩ሺ ወቄት ወርቅ መገበሩን ያስረዳል (2) ።

ስለዚህ ወዚር አዶሌ የዳሞትን ፤ የጋፋትን አገሮች ካስገበረ በኋላ በግራኝ አህመድ ትእዛዝ ከዳሞት ወደ ደብረ ብርሃን መጥቶ እስረኛውን በለው ሰገድን አቀ ረበውና በግራኝ ትእዛዝ አንገቱን ተቆርጦ ሞተ ። ይኸም በለው ሰገድ ከሁለት ዓመት በፊት በአይፈርስ (ዛሬ) ሲዋጋ የሞተው የራስ እስላም ሰገድ ወንድም ነው (3) ።

የጋፋትና የዳሞት ሕዝብ በቀላሉ ለወዚር አዶሌ መገበሩ የሚያስደንቅ አይደ ለም ። ከሁለት ዓመት በፊት ከአይፈርስና ከዝሆን ዱር ጦርነት በኋላ የዳሞት ፣ የጋፋት ፤ የጉራጌ ሕዝብ በራስ ወሰን ሰገድ ውስጥ ተሰብስቦ መጥቶ ከግራኝ ጋር በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በነሐሴ ፫ ቀን በተደረገው ጦርነት ተካፍሎ የታላቁንና የስመ ጥሩውን ገዥውን የራስ ወሰን ሰገድንና የሌሎቹንም ውጊያና አሟሟት አይቶ ታል ። ከመካከላቸው በዚህ ጦርነት ብዙዎች እንደሚሞቱ የታወቀ ነው ። የተረ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 397 - 398
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 398 - 399
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 399 - 400

ፋት ወደየአገራቸው ገብተው የእስላሞቹን አወጋግና አሸናፊነታቸውን ለየወገና ቸው ማውራታቸው የማይጠረጠር ነው ። ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት ወዲህ ግራኝ ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ በዋስል በሐይቅ በንጉሡና በአብያተ ክርስቲያናቸው ላይ የፈጸመው በባሌው ጦርና በአዝማች አዳሉ ላይ የደረሰው ሁሉ ሊሠወራቸው አይ ችልም ።

ስለዚህ ባሁኑ ሰዓት ያህር ጕይታን እንቀበልም ብለው ቢዋጉ አምኖ የመጣባ ቸውን በለው ሰገድን አዘንግተው አሥረው ለባለ ጊዜው ሽም ለወዚር አዶሌ ቢሰጡ አያስደንቅም ። ዓረብ ፋቂህ የጋፋት ሕዝብ ትምህርትም ሃይማኖትም የሌ ለው አረመኔ ነው እንዳለው ለነርሱ ክርስቲያኑም እስላሙም ቢገዛ ግዴላቸውም ይሆናልና ቀድሞ በሥልጣን ላይ ለነበረው ለክርስቲያኑ መንግሥት የሚገብሩትን አሁን አዲሱን ድል አድራጊ እስላሙን እንቀበልም ብለው በመዋጋት ፈንታ እሺ ብለው ገብረዋል ማለት ነው ።

የወላሞ ሕዝብ ግን እንኳን ለውጭ ባዕድ ለቅርቡ ላፄ ምኒልክ እንኳን እስቸ ግሮ በግድ የገበረ አገር ስለሆነ እርሱና ክርሱ ወደ ደቡቡ ያለውን አገር ግራኝና ጦሩ በርቀቱም በማጡም ምክንያት ለጊዜው ችላ ብለው አሁን ከሁሉ የበለጠ የታ ሰበበት ንጉሡ ነገሥቱ ያሉበት የሰሜኑ ጦርነት ስለሆነ ግራኝ ከነጦሩ ወደዚያ ሲያ መራ እንመለከታለን ።

ISIC

## ምዕራፍ ፳፮
## በግድም ተክለ ሃይማኖት ያደረገው መከላከል ።

የኛ ታሪክ ነገሥት ከዚሀ በፊት እንዳመለከትነው ግራኝ በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. በጥቅ ምት ወደ ቤተ አምሐራ ዘምቶ ንጉሡን በዋስል በድንገት ወግቶ ከዋስል አባርሮ እንዚያን ስመ ጥሩ የነመካነ ሥላሴን አብያተ ክርስቲያናት ዘርፎ ካቃጠለ በሐ ይቅ የመካነ እስጢፋኖስን ገዳም ከበዘበዘ በኋላ አሁን እንደገና ባመቱ ወደቤተ አምሐራ እስኪመለስ ድረስ ከዓመት በላይ (ከጥር ፲፭፻፳፱ እስከ ማያዝያ ፲፭፻፴፩ ዓ. ም.) በደቡቡ ክፍል ግራኝ ያደረገውን የግዛት መስፋፋት ፣ አዝማች አዳሉ በባሌ ፣ አዝማች እስላም ያህር በወጅ ፣ እነአክሊል በወረባ ፣ እነዮናዳብ እነሰይፋ በዝቋላ ዙሪያ አሁንም በግድም እነተክለ ሃይማኖት ያደረጉትን ተጋድሎ በሙሉ ዘሎታል ። የቀረው ቢቀር ሁኔታውን አንባቢ እንደተመለከተው የአዝማች አዳሉ ውጊያና ገድብዱ ሊዘለል አይገባውም ነበር ።

ያመቱን ታሪክ ዘሎ በቀጥታ ከሐይቅ እስጢፋኖስ ብዝበዛ ወደ ወርወር ብር በራ በመሻገር ባጭሩ እንደዚህ ብሎ ጠቅሶ አልፎታል "ይኸን ካደረገ በኋላ (ግራኝ አህመድ ማለቱ ነው) (1) ወደ አገሩ ተመልሶ ሄደ ። በዚያም ዓመት ከተቀመጠ

(1) ሐይቅ እስጢፋኖስን ከበዘበዘ በኋላ ማለቱ ነው ።

በኋላ በሚያዝያ ወር ተመልሶ ወርወርን በዘበዘ (1) ። በዚያን ጊዜ ልብነ ድንግል ከነገሡ ሐያ አምስተኛ ዓመታቸው ነው" (2) ።

በሚያዝያ ወር ተመልሶ መጣ ያለውና በዚህ ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል ከነገሡ ፳፰ ዓመት ይሆናቸዋል ያለው ትክክል ሲሆን "ወደ አገሩ ፥ ተመልሶ ሄደ" ያለው ስሕተት ነው ። አንባቢ ባለፉት ምዕራፎች የተጻፉትን እንደሚያስታውሰው በ፲፰፻ ፷፱ ዓ. ም. በጥቅምት ወር በዋሰል ዓፄ ልብነ ድንግልን አሸንፎ ከጥቅምት እስከ ጥር ወር ባለው ጊዜ ውስጥ እነዚያን ስመጥር አብያተ ክርስቲያናት (መካነ ሥላሴ ደብረ ነጐድጓድ) እየዘረፈ ካቃጠለ በሐይቅ የእስጢፋኖስን ገዳም ከአስበዘበዘ በኋላ በየካቲት ወር በታላቅ ሰልፍ በደብረ ብርሃን ከእንደራሴው ከወዚር አዶሌ ጋር እንደተገናኘ አንብበናል ። ቀጥሎም ከደብረ ብርሃን ወደ ወጅ ሄዶ በሚያዝያ የራማዳንን ጾም ካሳለፈና ወደ ጉራጌ አገር ሄዶ ጾሙን ከወገኖቹ ጋር ከገደፈ በኋላ እርሱ እንደ አንድ ንጉሥ በፈጠጋር በጉራጌ በሐድያ በወጅ እየተዘዋወረ ተዝናንቶ በመቀመጥ በዚሁ ጊዜ ፈራቃሃም ዲንን ጦር እየጨመረ በመላክ የዝቋላን የወጅን ዙሪያ በማስገበር ከቆየ በኋላ በነሐሴ ወር ደግሞ ወዚር አዶሌን ወደባሌ ልኮ ከአዝማች አዳሉ ጋር አዋግቶ ባሌን ካስገበረ ወዲህ በዚሁ በደቡቡ ኢትዮጵያ ከመቆየት በቀር ወደ ሀገሩ ወደ ሐረርጌ ወይም ወደማናቸውም ወደ አዳል ክፍል አልሄደም ።

ስለዚህ አሁን ደግሞ ዳሞትን እናርያን በአዶሌ ጋንዝን በአብድ ኢን ናስር እጅ የወላሞን አካባቢውን በሙጃሂድ ጦር ካስገበረ በኋላ ወላሞም ለጊዜው በማጦና በሕዝቡ ተከላካይነት የተነሣ ቢዘገይም ለጊዜው ግራኝ አህመድ በዚህ መስመር ያለው የማስገበር ጉዳይ ምንም ያህል የሚያስጋ ወይም ብዙ ጊዜ የሚወስድ አለመሆኑን ስለሚረዳ ግራና ቀኙ ሐድያ ጉራጌ ዳሞት እናርያ ከገበረ የወላሞ እም ቢተኝነት ምንም አስጊነት እንደሌለው በመገመት በሙሉ ለገበረው አገር የራሱን ሹማምንት በማሰባጠር የገበረውን አገር ባላባት እየደለደለ ከሾመ በኋላ እርሱ ባለፈው ዓመት በ፲፰፻፷፱ ዓ. ም.ዘምቶበት ወደነበረው ወደ አማራ አገር ጉዞውን ዠመረ ።

ከያለበት የተሰበሰበው ጦር ሠራዊት ደብረ ብርሃን ላይ ከከተተ በኋላ በመንዝና በግድም አድርጎ እንደምን እንደተጓዘ በመንገዱም የደገልሃን ልጅ ተክለ ሃይማኖት በምን አኳኋን ተቋቁሞ እንደተሸነፈ ዝርዝሩን ታሪክ ከዓረብ ፋቂህ እንደተለመደ እናንብብ ።

«ከዚህ በኋላ የእስላሞች ጦር ከነአለቃው ደብረ ብርሃን በተሰበሰበ ጊዜ ይማም አህመድ "እግዚአብሔር ይመስገን አበሻ ድል ሆነች ፥ ከትግሬ ፥ ከቤገምድር ፥ ከጐጃም በቀር ያልተገዛ የለም ። አሁን ግን ወደነዚሁ ወደቀሩት አገሮች ሂደን

(1) ወርወር የሚለው በሥፍራው ስንደርስ እንደምናመለክተው በላስታ ላሊበላ ያሳነጻቸውን መቅደሶች ነው ።
(2) ወዘንተ ገብር ሖረ ወተመይጠ ብሔሮ ወነበረ ዓመተ ፥ ወተመይጠ በወርኀ ሚያዝያ ወበርበረ ለወርወር ወክረመ በሕየ ። ወኮነ አሚሃ ፳ወ፭ ዓመተ መንግሥቱ ለልብነ ድንግል ። ታሪከ ነገሥት ሪጅ ባሴት ያሳተመው ገጽ 328 ፥

እንዋጋ ወይስ እዚሁ እያዝነው አገር አንድ ዓመት ተቀምጠን ሥራችንን እናደላ ድል የትኛው ይሻላል እስቲ ምከሩኝ” ብሎ ሹማምንቱን ጠየቀ ። ግማሾቹ እዚሁ አንድ ዓመት ወይም የበለጠ ቆይተን አደላድለን ስንጨርስ ከዚያ በኋላ ወደ አዘገ ኽን እንሄዳለን አሉት ፤ ሌሎቹ ደግሞ እንዘሐርቡይ መሐመድ ፤ እንወ፲ር አዶሴ ፤ እነወዚር ሙጋሂድ ፤ እነ አብድ ኢን ናስር “ይልቅስ አሁን ብዙ ወታደርና ኃይል እያለን ወደ ትግሬ ዘምተን ንጉሡን አለበት ድረስ እየተከታተልን ለመያዝ እንሞ ክር” ብለው መለሱ ይማም አህመድም “እውነታችሁን ነው” ብሎ የነዚህን የመ ጨረሻዎቹን አሳብ ተቀበለ ። ከዚህ በኋላ ፍሥሐ የሚባለውን የይፋት ተወላጅ በቅርብ ጊዜ የሰለመውን እንደርስብሃለንና ወደ ይፋት ሄደህ ቀድመህ ቆየን ብሎ ላከው ። አባስ ቤን አቡንን ሄደህ በግድምጌ (የግድም አገር) (1) ተቀመጥ ብሎ ላከው ። ኤሚር ሑሴንንም ወደ መንዝ አስቀድሞ ከነያኪም ጋር በቤተ አምሐራ መንገድ ወደ መንዝ ላካቸውና ቢሄዱ ምንም የጠላት ጦር አላገኙም ። እነዚህም ሁሉ በየክፍላቸው ከሄዱ በኋላ ይማም አህመድ ራሱ ወደ መንዝ ሄዶ ከኤሚር ሑሴን ጋር ተገናኘ ።

ገራድ አባስ ግን ግድምጌ ከገባ በኋላ ክርስቲያኖቹ ጓዝና ሀብታቸውን ልጅና ሚስቶቻቸውን ፈረስና ስንቃቸውን እንደያዙ ተራራ ይዘው ጢትና ማታ እየወጉ በጦርነት አደከሙት ። እርዳታም እንዳይደርስለት ይማም አህመድና እርሱ ባለ በት በኩል ያለውን መንገድ ዘግተው አስጨ[illegible] ። ይማም አህመድም በዚህ ሰዓት ከዋሰል በላይ በአንጎት ጫፍ ወደሚገኘው ወደ ሐይቅ ሄዶ ነበርና በዚያ ሳለ አባስ እንደዚህ የሚል መልእክት ላከበት “ክርስቲያኖቹ ተንኮል ሠርተው ባንተና በኔ መካከል ያለውን መንገድ ዘግተውታል ። በኔም ጦር ላይ ብዙ ጉዳት አድርገ ዋል ። እኔ ወደነሱ ሄጄ እንዳልወጋቸው ልደርስባቸው አልቻልሁም ፤ ስለዚህ ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ አንተ ባለህበት በኩል ተመልሰህ ውጋቸው እኔም በዚህ በኩል ዘምቼ ለሁለት እንውጋቸው ።”

የአባስ መላክተኛ ይኸን ደብዳቤ ይዞ ወደ ሐይቅ ሄዶ ለይማም ሰጠው ይማም “ክርስቲያኖቹ የትኛው ተራራ ላይ ነው ያሉት” ብሎ ቢጠይቀው “አንተ ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ዋሰል ላይ የተዋጋህ ጊዜ ራስ ደገልሃን መሸጎ ተቀምጦበት የነበረው እዚያው እግድም አገር ተራራ ነው እነዚህም ያሉት” ብሎ መለሰ ። “ዋና አለቃቸ ውስ ማን ይባላል” ቢለውም “በድምሩ አምስት አለቆች አሉ ፤ ባንደኛው ተራራ ሁለቱ ለብቻ ከነርሱም ጋር ያው ሹም ተክለ ሃይማኖት የሚባለው የራስ ደገል ሃን ልጅ ነው” ብሎ መለሰ ። ከዚህ በኋላ ይማም ዛሬ እዚሁ እንቆይ ነገ አንጎትን አስገብረን ከነገ ወዲያ ተደራጅተን ወደ ግድም እንሄዳለን አለና አብድ ኢን ናስርን ጨምሮ በኋላ የዚሁ አገር ግዛትን የተሾመውን ፋራቃሃም አሊን ወደ አንጎት ወደ በድል ናስር አገር ሄደህ የጦር አለቆች ከነጭፍራቸው አሉ ሲሉ ሰምቻለሁና ተዋጋ

(1) ግድምጌ የሚለው የግድም አገር ለማለት ነው ይኸውም ሐረር ሐረርጌ ፤ ጉርዓ ጉራጌ (ጉራዓገ) እንደማለት ነው ።

ብሎ አዘዘው ። ከዚያ ቀጥሎ ይማም "ስለዚህ ሹም (ስለ ተክለ ሃይማኖት) ምን ማድረግ የሚሻል ይመስላችኋል" ብሎ ቢጠይቅ አዶሌ እኔ ሄጄ ልዋጋው እለ "የለም አንተ እዚህ ቅር እኔ ነኝ ሄጄ የምወጋው" ቢል ኤሚር ሑሴን ደግሞ ኃይልም ብዙ ጦርም የላቸውም እና ለነርሱ ያንተን መሔድ አያስፈልግም እኔ እሄዳለሁ ብሎ ለይማም ቢመልስ የለም የዚህን ተራራ መንገድ የማውቀው እኔ ነኝ እና ንተ ብትሄዱ አይሆንላችሁም ስለዚህ ነገ ጉዞዬን እዠምራለሁ አዶሌ እዚሁ (ዜፈንታ) ቅር አለው ።

በማግስቱ በተከበረው በራማዳን ወር በ፱፻፴፱ የሂጂር ዓመት (1) ይማም አህመድ ፈጥኖ ተነሣና ጉዞውን ቀጥሎ ከዋስል በታች ሠፍሮ አዳሙሽን ይኸው በዚህኛው መንገድ ልንዋጋ መጥተናልና አንተም ባለህበት ወደፊት ግፋ ብሎ ወደ አባስ ላከበት ፤ ኤሚር ሑሴንን ደግሞ ወደቤተ አምሐራ ሄደህ ላይኛውን መንገድ ይዘህ ጠላትን ተጠባበቅ እኛም ታችኛውን መንገድ ሄደን ወግተን ድል እስክናደርጋቸው ድረስ ለመሸሽም ቢፈልጉ መንገድ አያገኙም ብሎ ላከው ። ከዚህ በኋላ ይማም ጉዞውን ቀጠለና እንጅማህ ምድር በሽሎ እዛፍ (በሽሎ አፋፍ - አብሽሎ ዘራፍ ?) እሚባለው ሥፍራ ላይ ሠፈረ ። በማግሥቱም የራማዳንን ጾም አቋርጡ (ተዉት ለዛሬ) ብሎ ለወታደሮቹ አዘዘና ወታደሮቹ ክርስቲያኖቹ ወደአሉበት ተራራ ሄደው በጧት ደረሱ ። የክርስቲያኖቹ አለቃ የእስላሞቹን ጦር ባየ ጊዜ ከተራራው ወርዶ ከበሩ በታች ወታደሩን ለውጊያ አሰለፈ ። በሩ ሁለት ስለ ነበረ ይማም ጦሩን እሁለት ላይ ከፍሎ አንዱን በግራ በኩል ያለውን በር ይዘህ ጠላትን ውጋ ብሎ ለሻሙን (ስምዖን) ሰጠውና እርሱ ራሱ የቀረውን ይዞ በቀኝ በኩል ወደ አለው በር ሄዶ መድፉን ከፈረሰኛው በፊት አስጠመደ ። አንድ ሰዓት ያህል እንደተዋጉ ክርስቲያኖቹ ከሁለቱም በር እየሸሹ ወደ ተራራው ጫፍ ድረስ ተመልሰው ወጡ ፡ እስላሞቹም እየተከታተሉ ሲወጡ ባንደኛው መንገድ በኩል ወርደው ለማምለጥ አሰበው ነበር ። ነገር ግን ከነርሱ ቀድሞ ኤሚር ሑሴን መንገዱን ይዞ ስለጠበቃቸው ማለፍ አልቻሉምና ከዚያ ተዘበራርቀው ይማም በያዘው በር በኩል ሲመጡ ከወታደሩ ጋር ሆኖ ሁሉንም ማረካቸው ። ቍጥራቸው አራት ሺህ የእግረኛ ጦር ይሆናል አለቃቸውም የደገልሃን ልጅ ነው ። እህመድም እንዲሰልም ቢጠይቀው እሺ ብሎ ሰለመና ከነምፍራው ከይማም ጋር አራት ወር ያህል እንደ ቆየ ዞብል አገር ቅዳ ከሚባለው ቦታ ሸሽቶ ጠፋ» (2) ።

በዚህ ምዕራፍ ያነበብነው ግራኝ አህመድ የደቡብ ኢትዮጵያን ግዛት ከአደላ ያለ በኋላ ወደ ሰሜን ሲዘምት እግረ መንገዱን በመዠመሪያ የፈጸመውን የግድ ምን ጦርነት ነው ። መቼም በደቡብ በኩል የግራኝ ኃይሉም ሥልጣኑም ደህና አድርጎ ስለተሰማና ስለታወቀ በእናሪያ በለው ስገድን ፡ በጋፋት ደሀርንትን (ደሀር ጎይታን ?) የወጋቸው የገዛ ያገራቸው ሕዝብ ነው ማለት ይቻላል ። የግራኝን አሸናፊ

(1) እንደ አው. ቀ. ሚያዝያ ወር ፲፭፻፴፫ እንደ ኢ.ት. ቀ. ፲፭፻፳፭ ሚያዝያ ፡
(2) ዓረብ ፋቂሆ ገጽ 400 - 404

ነት ስለአወቁ እርሱን ደስ ለማሰኘት ሲሉ የእናሪያው ባላባት በለው ሰገድ ወገኔ ነው ብሎ አምኖ ቢሄድበት መዝመሪያ አስተናግዶ በኋላም አዘንግቶ ይዞ ለአዶሌ እንደ ሰጠው ፤ አዶሌም ለግራኝ አስረክቦ እንዳስገደለው ፤ ደሀርጎትም ዳሞት ከአ ዶሌ ጋር መዋጋት ሳይሆንለት ቀርቶ ወደጋፋት ቢሄድ ወገኖቹ የማይቀበሉት ሆኖ እንዲያውም ያገሬው ሕዝብ ስለወጋው ከዚያ ሸሽቶ ንጉሡ ወደአሉበት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መሄዱን ባለፈው አንብበናል ።

ስለዚህ ግራኝ ወደ ሰሜን ዳግመኛ በሚጓዝበት ጊዜ ደንበኛ ጦርነት ከወዚር አባስና ቀጥሎም ከራሱ ከግራኝ ጋር የተዋጋው የአዛዥ ደገልሃን ልጅ ተክለ ሃይማ ኖት ነው ። ግድም እንደ እናርያ ፤ እንደጋፋት የሚቆጠር አገር ሳይሆን በፍጹም ያማራና የክርስቲያን አገር ስለሆን ሕዝቡ ከአለቃው ከተክለ ሃይማኖት ጋር አብሮ ግራኝን ተዋግቷል ማለት ነው ። ዳሩ ግን ግራኝና አባስ ግንኙነት አድርገው እየተላ ላኩ ፤ የጦር መላና ምቹ መንገድ እያማረጡ (በታክቲክ) በኅብረትና በመተሳሰብ ሲዋጉት በተክለ ሃይማኖትና በንጉሡ ባዬ ልብነ ድንግል ጦር መካከል ግንኙነቱ የተቋረጠ ይመስላል ። ያም ቢቀር ከአባቱ ከአዛዥ ደገልሃን ጋር እንኳን ግንኙነት አድርጎ የመሸሻ መንገድ እንኳን ሊከፍትለት የቻለ እርዳታ አላገኘም ። ምናልባት አባትዮው አዛዥ ደገልሃንም ባሁኑ ጊዜ የንጉሤን ሕይወት እጠብቃለሁ በማለት ከንጉሡ አልተለየም ይሆናል ። ስለዚህ ተክለ ሃይማኖት ግራኝ ባደረገው የጦር ዘዴ ዓይነት ግራና ቀኝ ረዳት ሳያገኝ ብቻውን በግድም ተራራ በየመስመሩ ተከቦ እስከ ተቻለው ብቻ ተዋግቶ በመጨረሻ ተማረከ ። ከ[illegible]ረከም በኋላ ግራኝ እንዲሰልም ጠየቀው እንጂ እንደሌሎቹ ከጦርነት ቦታ እንደተማረኩት የክርስቲያን አለቆች አልገደለውም ። አንዳንድ ጊዜ ለመስለም ፈቃደኛ የሆነው አይገደልም አንዳንድ ጊዜም ምንም ሳይጠየቅ የሚገደል አለ ። ተክለ ሃይማኖትን ያልገደለበት ምክንያት ተክለ ሃይማኖት የወጣት ዝግና ስለሆነ ወደፊት ከኔ ጋር አብሮ ለጦርነት ይረዳ ኛል ብሎ ይሁን ወይም በርሱ አማካይነት የንጉሡን ታላቅ የጦር አለቃ አዛዥ ደገ ልሃንን (አባቱን) አስከድቶ ለማስገባት ይጠቅመኛል ብሎ ይሁን አይታወቅም ። የሆነ ሆኖ ተክለ ሃይማኖት ለሁለቱም ለግራኝ ዓላማ መሣሪያ ሳይሆን ጊዜና ሥፍራ አማርጦ ዞብል የነበረ ጊዜ አምልጦ ወደ ወገኖቹ ሄደ ። በዚህ ደንበኛ ኢት ዮጵያዊ ክርስቲያን ፤ የንጉሡና የወገኖቹ ታማኝና የማያወላውል ጠባይ ያለው ሰው መሆኑን አስረዳ ።

## ምዕራፍ ፳፰

## የአምባ ግሼን ተራራ ፪ኛ መከበብና የክርስቲያኖች መመከት (፲፭፻፳፭ ዓ. ም. ግንቦት - ሰኔ)

ስለ አምባ ግሼን ከዚህ በፊት ጽፈናል ። በዚያም ግራኝ ወደ ቤተ አምሐራ ሄዶ እነመካነ ሥላሴን አቃጥሎ ሲጨርስ አንድ ባላገር ንጉሡ ከጥቂት ሰዎች ጋር

ያሉበትን እመራለሁ ብሎ ከሠፈር መጥቶ ስለተናገረ ገራድ አህሙሹ ጦር ይዞ ንጉሡን ተከታትሎ አጥቷቸው ሲመለስ መንገድ አሳብሮ አምባ ግሼንን ከቦ ሲወጋ ከኋላው እንቢትወደድ ሡርዬ ደርሰው የሠሩትን እንገብበናል ።

ስለዚህ ከዚህ በፊት ተሞክሮ ሳይቻል የቀረውን አሁን ግራኝ ራሱ ከደብረ ብርሃን ወደ ዋስል ከዋስል ወደ ግድም ሄዶ በተክለ ሃይማኖት ጦር ተከቦ የነበረውን የወንድሙን ልጅ ገራድ አባስን ነፃ አውጥቶ ተክለ ሃይማኖትን ከማረከ በኋላ ፊቱን ወደ ቤተ አምሐራ መልሶ ወደ አምባ ግሼን ጉዞውን ቀጠለ ። ከቀድሞው የበለጠ በአሁኑ ጊዜ ለወረራው የሚያገለግለው ጦርና የጦር መሣሪያ አዘጋጅቷል፣ በተለይ እንደ አምባ ግሼን የመሰለው የእግረኛና የፈረሰኛ ጦር እንደልቡ ወጥቶ ሊዋጋበት የማይችል መሆኑን በመረዳት ቀደም አድርጎ ውርጂ አቡን የሚባለውን ወደ ዘይላ ወደብ ልኮ አንድ ትልቅ ከመዳብ የተሠራ ሁለት ትናንሽ ከብረት የተሠሩ መድፎች አስገዝቶ ከሁለት የሕንድ መድፈኞች ጋር አስመጥቷል ።

መድፎቹም ከዘይላ እስከ ግንደበሎ (ይፋት) በግመል ከመጡ በኋላ በግድም በኩል ሲመጡ አገሩ ከገደላ ገደልነቱ የተነሣ በግመል እንኳን መጫን ሳይቻል ቀርቶ አብዛኛው ጊዜ በሰው ትከሻ አልፈው ከዚያ በአባስ መሪነት መድፎቹ ከመድፈኞቻቸው ጋር በደህና ይማም ከሠፈረበት ከአምባ ግሼን አጠገብ መድረሳቸውን ዓረብ ፋቂህ ይገልጻል ።

በዚህም ጊዜ አምና በተደረገው ጦርነት እነገራድ አህሙሹ ፤ እነኡስማን እላይ ከአሉት ጋር ሲዋጉ ከኋላ የንጉሡ ጦር መጥቶ ሊያጠቃቸው የቻለ መሆኑን ስለሚያውቅ የመጣው ጦሩ ከተራራው ካሉት ሰዎች ጋር ሲዋጉ ግራኝ ባንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ ከውጭ የሚመጣ የጠላት ጦር እየተመለከተ ይቆጣጠር እንደነበረ በበኩላቸው ንጉሡ ነገሥቱ ይኸን አምባ ለመከላከል ወደ ትግሬ መኳንንትና ፈረሰኛ ልከው እንደነበረ ከነርሱም ውስጥ አዝማች ኤሚርና የባሕር አምባ (ሰሜን) ገዥ ተስፋ ኢየሱስ እንደዚሁም ጠበንጃና መድፍ ይዘው የሚዋጉ ሁለት የዓረብ ተወላጆች አንዱ ሐሰን ኤል ባስሪ ሁለተኛው አብድ አስፋር ተርኪ የሚባሉ እንደነበሩ ፤ እነዚህም ቀደም ብለው ተራራውን ይዘው ሲጠባበቁ እነዚህ ከላይ እነዚያ ከታች ሆነው ሲዋጉ የሁለት ወር ጊዜ ማለፉን በመጨረሻም ግራኝና ጦሩ የናዳ በረዶ እየወረደባቸው ወደ ተራራው መውጣት ችለው የታችኛውን ክፍል ሲይዙ በተደረገው ጦርነት አዝማች አሚር ሲሸሽ ዓይኑን በመድፍ እንደተመታ ተስፋ ኢየሱስም ሲሸሽ ሆዱን ተመትቶ እንደሞተ ይገልጻል (1) ።

በዚህ ጊዜ እየሸሹ ወደላይኛው ክፍል የወጡትን ክርስቲያኖች ደህና አድርገው በመድፍ እንዲመቱዋቸው ለነዚህ ለሁለቱ የሕንድ መድፈኞች ፩፻ ወቄት ወርቅ ፤ የተራራ ጦርነት ለሚያውቁ የእግረኛ ወታደሮች ለየአንዳንዳቸው የወርቅ አምባር በጉርሻ ስም አድሎ በበላያቸው ዘሐርቡይ መሐመድን ባንደኛው በር ሾሞ ለሌላው በር ደግሞ ገራድ ሻሙንን ካደረገ በኋላ መድፈኞቹን "እነዚህ መንገድ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 407 - 408

ይዘው እንዳናልፍ፡ በሚከላከሉን ላይ ተኩሱባቸውና ወደላይ እንድንወጣ" ብሎ ለቀሩትም ለሁለቱ የጦር አለቆች በሉ እንግዲህ ይኸን አምባ ከባችሁ ውጉ የሚል ትእዛዝ ሰጠ ።

ከዚህ በኋላ እላይና እታች ያሉት በመድፍም በናዳም እየተዋጉ ከዉት የገፖመ ረው ጦርነት እስከ ማታ ድረስ ከቀጠለ በኋላ ግራኝ በመጨረሻ ይኸን አምባ ከቦ መውጋት ለኛ ምንም ረብ የለውም እንግዲህ በቃችሁ ብሎ ለሚዋጉት ትእዛዝ ሰጥቶ ወደ ሠፈር መልስ መሆኑን ዓረብ ፋቂህ ያመለክታል ።

ግራኝ በዚህ ዓይነት በመዠመሪያ ላይ ተዋግቶ ዝቅተኛውን ክፍል በመያዝ እነዚያን ስማቸውን የጠቀሰውን የትግሬ ሹማምንት ቢገድልም መደምደሚያውን የላይኛውን ክፍል የነገሥታት ልጆች ያሉበትን መያዝ አቅቶት እንደተመለሰ ይታ ያል ። የግራኝ አህመድ ከችሎታዎቹ አንዱ እልሁን ለመግታት መቻሉ ነው ። እር ሱም እንደ መልካም የጦር መሪ ምቹውን ሥፍራ መርምሮ የተዋጊን መንፈስ በስ ጦታም በንግግርም ከሞላ በኋላ በኃይልና በድፍረት ይዋጋል ። በሩቅ መሪ ትእዛዝ ሰጭ ብቻ ሳይሆን በቅርብ በጥናት ተከታትሎ ሁሉንም እየተቆጣጠረ እዋጊም ተዋ ጊም ስለሆነ የውጊያው አዝማሚያ ወደ ድል ጐዳና የማያመራ መሆኑን ሲገነዘበው ደግሞ በእልህ በርታ በለው እያለ ወታደር በማስጨረስ ፈንታ የለም በቃ የሚል ትእዛዝ በመስጠት በጥንቃቄ የወታደርን ሕይወት ከማትረፍ ጋር የመሣሪያ ቁጠባ ያደርጋል ። ዓላማው ሩቅ ነው ። ትግሬና አንዳንድ ጐጃምና ቤገምድር በፊቱ እንዳሉ ያውቃል ። የንጉሡ እስካሁን በሕይወት መኖር ለዓላማው መሰናክል እንደሚሆን በት እርሳቸውም ለአልተያዙት አገሮች አለኝታና ተስፋ እንደሆኑ በርሳቸውም ዙሪያ ብዙ ጦር እንዳለ ያውቃል ።

ስለዚህ በዚህ ተራራ የወታደርን ኃይል ከማድከምና የጦር መሣሪያን ከማባ ከን ይልቅ ይኸን እንዳለ ወደኋላ ትቶ ወደፊት ቀድሞ እነዚያን ሲያሸንፍ የእዚህ ኛው ውድቀት አውቆ የሚከተል መሆኑን ሳያመዛዝን የሚቀር አይመስልም ። በዚህ ምክንያት ከደረሰበት ተራራ ላይ ፊቱን ወደኋላ መልሶ ወደታች ወርዶ ከሠ ፈሩ እርፎ በማግሥቱ ጉዞውን ወደ እንጎት ቀጠለ ። እንጎት ግራኝ አህመድ በወረ ረበት ሰዓት ከዛሬው የጁ ወደ ሰሜን ከዋጅራትና ከአምባ አላጌ በደቡብ ከላስታ ወደ ምሥራቅ ደቡብ ሲል ያለ ቀድሞ ታላላቅ ሰዎች የሚሾሙበት ታላቅ አውራጃ ነው ። የዛሬን የወሎን ሰሜን የላስታንም ክፍል የደረበበት ጊዜ አለ ። በአይፈርስ ጦርነት ጠቅላይ አዝማች ሆኖ ራስ እስላም ሰገድን በውስጡ አድርጎ ተዋግቶ የሞ ተው ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ የእንጎት ገዥ እንደነበረ በአይፈርስ ጦርነት ያነበብነውን እናስታውሳለን ።

ዓረብ ፋቂህ በዚህ ተራራ ላይ ከተዋጉት ሹማምንት አንዱን አዝማች ኤሚር ሲለው ሁለቱን ደግሞ መድፍና ጠበንጃ ተኳሾች ዓረቦች አድርጓቸዋል ። እነዚ ህም ከሐረር ከሱልጣኖቹ ጋር እየተጣሉ ወዲህ መጥተው ለንጉሡ ነገሥቱ ያደሩ ይሆኑ ወይም በምጥዋና በደባርዋ የሚኖሩ የንጉሡ ነገሥቱ ዜጎች ይሁኑ በትክክል አይታወቅም ። በነርሱ እጅ ያለው መድፍና ጠበንጃ ምናልባት ከብዙ ዓመት በፊት

በዘይላ ይሁን ወይም በምጥዋ በኩል ተገዝቶ የመጣ አሮጌ መድፍና ጠበንጃ ይሆ ናል እንጂ ደህና አድርጎ የሚያገለግል አዲስ መድፍ ሊሆን አይችልም ። ዓረብ ፋቂህ መተኰሱን ሲናገር ጉዳት ማድረሱን በፍጹም አይናገርም ።


በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መካከል በተወጠነው ወዳጅነት በቱርክና በፖር ቱጋል ጠብ በቱርክ ማየልና ወደቦቹን መቆጣጠር የተነሣ እንአልቫሬጽ ከተመለ ሱና ጦርነቱ ከተዠመረ አንሥቶ በተለይ ባሁኑ ጊዜ የመሣሪያ ማግኛው በርና ወደብ ሁሉ ለግራኝ የተከፈተው ላዔ ልብነ ድንግል መንግሥት ደህና አድርጎ ተዘ ግቷል ። ስለዚህ አሁን ዓፄ ልብነ ድንግል ከደዋሮ ዠምሮ እያባረረ እስከ እሉበት እስከ አማራውና እስከ ትግሬው አገር ድረስ መጥቶ ከሚወጋቸው ከግራኝ እህ መድ ጋር የሚያደርጉት ጦርነት መውጫና መግቢያ በሌለው በተዘጋ ቤት ነው ማለት ይቻላል ። መግቢያና መውጫው በኋላ በፖርቱጋሎች እስኪከፈት ድረስ ተስፋ በሚያስቆርጥ አኳኋን ሲመች መከላከሉን ሳይመች ካገር ወዳገር መሰደዱን ከመቀበል ሌላ ተስፋ የላቸውም ።

## ምዕራፍ ፳፱
## በላስታ የላሊበላ ቤተ ክርስቲያን መበዝበዝ
ISI(፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ሰኔ - ሐምሌ ) ።

ግራኝ አህመድ በግሼን አምባ አጠገብ በዚሁ በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በሚያዝያ ወር የራ ማዳንን ጾም ከፈታ በኋላ ወደ አምባው ሄዶ ሁለቱን የግንቦትንና የሰኔን ወራት አምባውን ከቦ መደምሰስ ሳይሆንለት ቀርቶ ከቢውንና ውጊያውን ትቶ ወደ ላስታ አቀና ፤ በዚያም ላሊበላ ያሠራቸውን አብያተ ክርስቲያናት ሲዘርፍ እናያለን ። የግ ዕዙ ታሪክ ነገሥት አሁንም የአምባ ግሼኑን የከቢ ጦርነት በመዝለል ፤ በላሊበላ ዘረፋም ጊዜ የሆነውን ዝርዝር አድራጐት በመተው ፤ ባለፈው በሚያዝያ ወር ከሸዋ ተመለሰ በማለት ፈንታ አገሩ ዓመት ከርሞ ተመለሰ ካለው ቀጥሎ "ወር ወርን በዘበዘ" ብሎ ረዥሙን የታሪክ ምዕራፍ ቀንጠብ አድርጐት አልፏል (1) ። በአነጋገሩም በዘበዘው ይላል እንጂ በላስታ የላሊበላን አብያተ ክርስቲያን አቃጠለ አይልም ። "እውአየ - አቃጠላት" በማለት ፈንታ "በርበረ - በዘበዛት" ማለቱ የላሊበላ ሕንፃዎች ሥራ ጣራውም ግድግዳውም ሁሉ በሙሉ ከደንጊያ ቋጥኝ ተፈ ልፍሎ የተሠራ ፈጽሞ የደንጊያ ሕንፃ ስለሆነ እንደሌሎቹ ሁሉ ለማቃጠል ሳይ ቻል መቅረቱን ሲያመለክት ነው ።

ይህ ግዕዙ የወርወር ቤተ ክርስቲያን የሚለው የዛጕዬው ንጉሥ ዓፄ ላሊበላ

(1) ታሪከ ነገሥት ወተመይጠ በወርኃ ሚያዝያ ወበርበረ ለወርወር ሲል ከደብረ ብርሃን የተመለሰበ ትን ሚያዝያን ማለቱ ነው እንጂ የበዘበዘው ግን በሰኔ ወይም በሐምሌ ይመስላል ።



ይህ ሕንፃ ምንም ከላይ ቢታይ የሴሎቹን ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት የሕንፃ ዓይነት ያመለክታል ።

ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት በሕዝብ ዘንድ የተከበሩ የጥፉተኛ መማጠኛ ሆነው ኖረዋል ።

ዮናኤል የሚባለው ሹም ባዔ ሱስንዮስ (፲፭፻፺፱ - ፲፮፻፳፩ ዓ. ም.) ላይ የሸፈተ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ እርሱን ሊወጉ ወደ እንጎት በሄዱበት ሰዓት የዮናኤል ጭፍሮች በምሥጢር ከንጉሠ ነገሥቱ ተላልከው ጌታቸውን ከድተው በገቡ ጊዜ "ክርሱ እንደምን ተለይታችሁ መምጣት ቻላችሁ" ብለው ንጉሡ ቢጠይቁዋቸው መሸመሪያ እባክህ በወርወር ቤተ ክርስቲያን ተማጠንና ከጌታህ ታረቅ ብለን ብንለምነው እምቢ ስላለ ትተነው መጣን ብለው እንደ መለሱ አዛዥ ተክለ ሥላሴ (ጢኖ) ያዘጋጀውና የፖርቱጋሉ ተወላጅ ፔሬይራ ያሳተመው ያዔ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ያረጋግጣል (1) ።

በዚሁ ምዕራፍ ላይ ዓፄ ሱስንዮስ ወደ እንጎት የመጡ ጊዜ በመንገድ ሳሉ ዓፄ ይኩኖ አምላክ ከሣርም ከእንጨትም ከግንብም ሳይሆን ቀዩን የደንጊያ ቋጥኝ አስጠርበው ያሠሩትን ቤተ ክርስቲያን ወና ሆኖ አግኝተውት ተሣለሙ ይላል (2) ።

ይህ ታሪካዊ ሕንፃ እንደ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ ቅርስ ሆነው ዛሬ በዚሁ ቦታ መኖራቸውን አላረጋገጥም ። በአገር ተወላጅም በውጭም አገር ሰው ስሙና ዝናው ሲጠራ እምብዛም አይሰማም ።

ስለዚህ ታሪከ ነገሥቱን ያዘጋጀው ካህን "ወበርበራ ለወርወር" ሲል ዓፄ ላሊበላ በላስታ ያሠራውን ሕንፃ እንጂ ይኩኖ አምላክ በእንጎት ያሠራውን ይኸን ሕንፃ አይደለም ። እነዚህ የላሊበላ ሕንፃዎች ያሉበት ወረዳ ከቀድሞ ዠምሮ በጐንደር መንግሥት ጊዜ ሁሉ ወርወር መባሉን ለማስረዳት ስለዓፄ ተክለ ጊዮርጊስ (ፍቅር ሰገድ) የተጻፈው ታሪከ ነገሥት "ንጉሡ ወርወር ወደምትባለው ወደ ላሊበላ ገባ" ይላል (3) ። በጐንደር ዘመነ መንግሥት ላስታን ደርቦ የሚገዛው የቤገምድር ገዥ የማዕርግ ስሙ በግዕዝኛ "ቤገምድር አዝማች ሊቀ ካህናት ዘወርወር" ይባላል ። ይኸውም ማለት ቤገምድርን እየገዛ በሥጋዊ አስተዳደሩ ላይ ላስታ በቤገምድር ውስጥ በሚቆጠርበት ጊዜ የወርወር ሊቀ ካህናት እየተባለ የቤተ ክህነቱን ወይም መንፈሳዊውን ተግባር ደርቦ ይይዛል ። በዚሁ ዓይነት የአማራው ገዥ በትረያሬክ እየተባለ የተድባበ ማርያምን ዕልቅና ደርቦ ይይዛል (4) ። ነገር ግን እነዚህ አገረ ገዥዎች ሥያሜውን ይያዙ እንጂ በቅርብ ሆኖ ተግባሩን የሚፈጽም ካህን በየአንዳንዳቸው እናት ላይ እንደሚኖር የታወቀ ነው ። በቀድሞ ጊዜ ወርወር እንደወረዳ ሆኖ ከተማው ሮሀ ነበር ።

ላሊበላ በዘመኑ ስላሠራቸው ዛሬ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ የውጭ አገር

(1) Chronica de Susenyose Pereira ምዕ. 62 ገጽ 246 - 248

(2) ወረከበ በፍኖት ቤተ ክርስቲያን ብድውተ ዘአሕነፃ ንጉሥ ይኵኖ አምላክ አኮ በዕፅ ወበሣዕር ወአኮ በንድቅ አላ ውቅርት ይእቲ እምዕብን ቀይሕ ብዙኅ እዕማዲሃ ወብዙኅ ኅዋኅዊሃ ወቦዓ ንጉሥ ወተአምኃ ወወሀበ ሀብተ በረከት ይላል ።

(3) ታሪከ ነገሥት ገጽ 344 ፲ኛ አምድ ወቦአ ላሊበላ ዘትሰመይ ወርወር ።

(4) የበካፋና የኢያሱ ዜና መዋዕል ጉይዲ ያሳተመው ክፍል 3 ገጽ 293 ።

ጐብኝ እየተመለከተ ስለሚያደንቃቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ስለሥራቸው ማማርና አስደናቂነት ጽፈዋል ። ከነዚህም ዋነኞቹ ፍራንቼ ስኮ አልቫሬጽ (Francesco Alvarez) ገርራር ሮልፍስ (Gerhard Rolphs) አሺል ራፍሬይ (Achile Rafray) ገብርኤል ስምዖን (Gebriel Simon) ናቸው (1) ።

ስለዚህ አሁን ግራኝ አህመድ የንጉሡ ጦር አለ ወደሚባልበት ወደ ትግሬ ሲዘ ምት እግረ መንገዱን ላስታ ደርሶ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት በምን አኳኋን እንደበዘበዘ ከታሪክ ነገሥቱ በተሻለ አኳኋን ዓረብ ፋቂህ እንደዚህ ሲል ጽፎታል። «በዚሁ በቅዳ ጓዙን ከወዚር አዶሌ ጋር ተወና እርሱ ወደ ትግሬ ሄደ ። በመንገድም ሳለ ክርስቲያኖቹ ላሊበላ እሚባለው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ተሰብስበዋል ማለ ትን ስለሰማ በተራራና በአስቸጋሪ መንገድ አልፎ ወደ ላሊበላ ጉዞ ዝ መረ ዝናምም ይዘንም ነበር ሌሊቱን ሁሉ ሲጓዙ ከብርዱ የተነሣ ብዙ ሰው ሞተ ።

ላሊበላ በደረሰ ጊዜ ስለቤተ ክርስቲያኑ (ስለሃይማኖታቸው) ለመሞት እቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ብዙ መነኮሳት ተሰብስበው ነበር ። ይማም ከዚህ ቀደም በየ ትም አገር ዓይቶ የማያውቀውን ቤተ ክርስቲያን ተመለከተ ። ቤተ ክርስቲያኗ የተ ቀረጸችው እተራራ ውስጥ ነው ። ዓምዶቿም (ከደንጊያ) የተቀረጹ ነበሩ ። በውስጡ ከታቦታቸው በቀር የእንጨት ሥራ የለበትም ።

ይማም ቀሳውስቱን ከሰበሰበ በኋላ እንጨት አስቆልሎ እሳት አስነደደ ። እሳቱ በጣም ተያይዞ ሲንቦገቦግ "በሉ እንግዲህ ከናንተ አንድ ሰው ምረጡና ከኛም አንድ ሰው መርጠን ሁለቱ ከዚህ ከእሳቱ ውስጥ ይግቡ" ብሎ ቀሳውስቱ የሚያደርጉትን ለማወቅና ለመፈተን ሲል ሲጠይቃቸው የቀሳውስቱ አለቃ "መል ካም ነው እኔ እገባለሁ" አለ ። በዚያን ጊዜ አንዲት በሃይማኖት ሥራ የምትኖር (መነኵሲት) ሴት "የወንጌል መምህራችን ተቃጥሎ ሲሞት አላይም" ብላ ተወር ውራ ወደ ነበልባሉ ገባች ። በዚያን ጊዜ ይማም "ጐትታችሁ አውጧት" ብሎ አዘ ዘና አወጧት ። ስትወጣ ግማሽ ፊቷ ተቃጥሎ ነበር ።

ISLC

ከዚህ በኋላ ታቦታቱ ተቃጠሉ እንደ ጣዖት የሚያመልኩበት የደንጊየ ሥራ ተሰባበረ ። የተገኘው የወርቅ ሥራና የሐር ልብስ ሥጋጃ ተወሰደ» ሲል ዓረብ ፋቂህ የላሊበላን ቤተ ክርስቲያን ብዝበዛ እዚህ ላይ ያቆምና ወደ ትግሬው የዘመቻ ጉዞ ይተላለፋል (2) ።

ዓረብ ፋቂህ በዚህም በሌላም ቦታ በመጽሐፉ ላይ ታቦታቱን ሥዕሎቹን መልክ ያላቸውን ቅርጾች ሁሉ ጣዖታት ይላቸዋል ። በክብረ በዓል ቀን ቀሳውስቱ ተሸክመው በወጡበት ቀን ሕዝበ ክርስቲያኑ በታቦት ፊት መስገዱን ሥዕለ ማር ያም ፤ ሥዕለ ጊዮርጊስም ሲያይ እጅ መንሳቱን ስለሚያውቅ በራሱ አጠራር ይኸን የሚያደርጉትን ክርስቲያኖቹን ጣዖት አምላኪዎች ይላቸዋል ።

(1) የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ . . . . . ምዕ. 79

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 410 - 413

ይኸንንም ከማለት የሚያደርሰው አይሁዶቹም ክርስቲያኖቹም እስላሞችም በሚያምኑበት በኦሪት ውስጥ በተለይ በዘፀዐት ፤ በዘሌዋውያን ላይ ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ በፊቴ ሥዕልንም ምሳሌንም ላንተ አታድርግ የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው (1) ። በተለይ ደግሞ መሐመድ በዓረብ አገር የእግዚአብሔርን አምላክነት የመሠረተው ክርስ በፊት ሕዝቡ ያመልክባቸው የነበረውን የፀሐይ ፤ የጨረቃ ፤ የከዋክብት የጣዖት አማልክት በብዙ ውጊያ አጥፍቶ ስለሆነ በዚሁም አምልኮን በሱራት ፶፩ ቊ. ፭ በሱራት ፶፫ ቊ. ፷፪ በሱራት ፵፩ ቊ. ፴፯ ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ስለሚያዝ (2) ዓረብ ፋቂህ በመካነ ሥላሴ ቃጠሎ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሦስትነት መቃወሙን እንዳመለከተ የደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም መምህር የተገናኙትለት አጉንብሰው እጅ ቢነሡት "ምስኪን ለሰው አትስገድ" ብሎ ግራኝ የተቆጣው ከዚሁ አሳብ ጋር የተያያዘ ነው ። ነገር ግን በኛ በኩል ሁሉም መልስ አለው ። ለሰው እጅ መንሣት አክብሮት ነው ፤ ሥላሴም በአካላት ሦስት ይሁኑ እንጂ በመለኮት አንድ ናቸው ።

በተረፈ ዓፄ ላሊበላ በ፲፪ኛው መቶ ዓ. ም. መጨረሻ (ወይም በ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. መገመሪያ) ላይ ከግብፅ አገር የእስላሞቹ አጥቂነት አስመርሯቸው ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው በመጡት የግብፅ ክርስቲያኖች እርዳታ በላስታ ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት ቊጥራቸው ፲፩ ስማቸውም ቤተ ደናግል ፤ ቤተ ማርያም ፤ ቤተ መድኃኔ ዓለም ፤ ቤተ መስቀል ፤ ቤተ ጎልጎታ ፤ ቤተ ቅዱስ ሚካኤል ፤ ቤተ ገብርኤል ፤ ቤተ አባ ሊባኖስ (አባ መጣዕ ባለቤቱ መስቀል ክብራ ስለባሏ ክብር ያሠራችው) ፤ ቤተ መርቆሬዎስ ፤ ቤተ አማኑኤል ፤ ቤተ ጊዮርጊስ ሲሆን ዓረብ ፋቂህ በአጸፋ ላይ የሚያሳየው በብዛት ሳይሆን ባንድ በነጠላ ቤተ ክርስቲያን አስመስሎ ነው ።

የዚህ ምክንያት ምናልባት ዘረፋውን ሁሉም አብያተ ክርስቲያን ተዘርፈው ካህናቱና ቀሳውስቱ ለሞታቸው ቆርጠው የተሰበሰቡት ግን ላሊበላ በተቀበረበት ባንዱ በቤተ ጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን በራፍ ላይ ይሆናል ። ለመፈተን ሲል አሽናፊ ውና በዚህ ሰዓት ዘመናይነት የሚሰማው ግራኝ አህመድ እንጩት አስረብርቦ እሳት አስነድዶ ማነው ከመካከላችሁ ከኛ ሰው ጋር ገብቶ ሊቃጠል የቀረጠ ብሎ የጠየቀው በሁሉ ሥፍራ ላይ ስለማይችል በዚሁ በጎልጎታ ላይ ብቻ ይሆናል ።

ግራኝ የደብረ ሊባኖስ ገዳም የአትሮንስ ማርያም ፤ የቤተ ሰማያት አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ ብዙ መነኮሳት እነበልባሉ ውስጥ እየገቡ መሞታቸውን በወሬ ሰማ እንጂ በዓይኑ ያየ አይመስልም ። የላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ግን ራሱ በሥፍራው የነበረው ዓረብ ፋቂህ እንዳለው ከታቦታቱ በቀር ጣራውም ግድግዳውም የደንጊያ ሕንፃ ሆኖ በፍጹም እንጩት ስለሌለበት እስላሞቹና መሪው አህመድ እንደቀሩት የአውራጃዎች አብያተ ክርስቲያናት ሀብቱን ዘርፈው ሲጨርሱ

(1) ዘፀዓት ምዕ. 20 ቊ. 3 - 5 ዘሌዋውያን ምዕ. 26 ቊ. 1
(2) ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊ ሙሴ ረጂስ ብላንሼር የተረጐሙትን የቁራን መጽሐፍ ተመልከት ።

እሳት ለኩሰው ቤተ ክርስቲያኑ ተያይዞ ነበልባሉ በሚንቀለቀልበት ጊዜ መነኮሳቱ በውስጡ ገብተው ለመቃጠል መቁረጥ አለመቁረጣቸውን ሊመለከቱ አልቻሉም ።

ስለዚህ ግራኝ እንጨት አሰብስቦ ባንድ ሥፍራ አስቆልሎ ካስነደደ በኋላ ለመ ፈተን "ከናንተ አንድ ክርስቲያን ከኛም አንድ እስላም ሁለቱ ገብተው ይቃጠሉ" ቢል የቤተ ክርስቲያኑ እለቃ ሳያወላውሉ እሺ መልካም ነው እኔ እለሁ ብለው ለመ ቃጠል ሲዘጋጁ ባጠገባቸው ያሉ አንዲት መነኵሲት መምህራችን ሲቃጠሉ እላ ይም ብለው ዘለው ሲገቡ በእስላሞቹ ፊት የክርስትና ሃይማኖታቸውን ጽናት ለስማዕትነት ያላቸውን ቁርጠኛ ፈቃድ ገለጹ ማለት ነው ። ይህ ከሆነ በኋላ ሴቷን መነኵሲት አስወጥቶ መምህሩን ያቃጥላቸው ወይም ይማራቸው ጽሕፈቱ በትክክል አይገልጽም ። ነገሩን ያመጣው እንደ ምሥራቅ ሃይማኖት ልማድ ለመፈ ተን ነውና ተጠይቀው ለመቃጠል በፍጹም መቁረጣቸውን በተረዳው ጊዜ እርሳ ቸውን ትቶ ታቦታቱን ብቻ ያቃጠለ ይመስላል ።

የምሥራቅ ልማድ ያልነውም ኤልያስ የአክአብን ሚስት ኤልዛቤልን የአን ቺም የጣዖት ካህናት በሬ ይረዱ እኔም ለአምላኬ የምሠዋው በሬ አርጂ የሁለታች ንን መሥዋዕት በተረበረበ እንጨት ላይ አድርገን እናቃጥልና እግዚአብሔር የማና ችንን መስዋዕት እንደሚቀበል እናስመስክር እንዳለው ሁሉ (1) በፋርስ በዓረብ አገር በሃይማኖት የሚከራከር ሁሉ እሳት አንድደን ከየወገናችን ሰው እንጨምርና ሳይቃጠል የዳነው እውነተኛ ባለ ሃይማኖት[illegible]ው እየተባባሉ ግማሾቹ ተቃጠሉ ግማሾቹ ዳኑ እየተባለ በየመጽሐፋቸው ጽፈዋል ።

ግራኝ ግን የላሊበላ መነኮሳት ፈርተው እምቢ ቢሉ ኖሮ ለመግቅና ለመግ ለቅ ወይም ከፈራችሁ ብሎ ለመግደል ይሆናል እንጂ ከራሱ ወገን አንድም እስላም መርጦ ሊያቃጥል እንደማይፈልግ የታወቀ ነው ። ነገሩንም ያመጣው ለፈተና ብቻ መሆኑን የዓረቡ ጸሐፊ ገልጾልናል ።

## ምዕራፍ ፹

### የግራኝ አህመድ ጉዞ ወደ ትግሬ ፤ የዘሐርቡይ መሐመድ ሞት (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. መስከረም)

ታሪክ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ካመለከትነው በማያያዝ ባመቱ ተመልሶ ወርወርን (የላ ሊበላን ቤተ ክርስቲያን) በዝብዞ በዚያው ክረምትን ማሳለፋን በዚህም ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል ከነገሡ ፳፭ ዓመት መሆኑን ከአመለከተው እያይዞ ባመቱ ንጉሡ በነገሡ በ፳፮ኛው ዓመት በጥቅምት ወር ግራኝ ወደ ትግሬ ሄዶ የሽሬና የሠራዬ አገር እንደተቀበለው ። ንጉሡ ግን በደምቢያ ክረምትን አሣልፈው ከዚያ በጥቅ ምት ወር ወደ ወገራ ሄደው ከዚያም በታኅሣሥ ወር በጸለምት በኩል አልፈው በ፲፭

(1) መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕ. 18

ቀን የጥምቀትን በዓል አክሱም ላይ ማክበራቸውን ያመለክታል (1) ።

ታሪክ ነገሥቱ በጣም በማሳጠር የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ በሰፊ በመዘርዘር ከመለያየታቸው ወይም ካንዳንድ ጥቃቅን ሁኔታ በቀር በጠቅላላው በታሪኩም በወሩና ባመቱም የሁለቱ ጽሑፍ መስማማት ለጸሐፊም ለአንባቢም ደስ ያሰኛል ። ታሪክ ነገሥት እንዳነበብነው ግራኝን የሺሬና የሠራዬ ሰው ተቀበለው ያለው በኑሮውና በትዳሩ ምክንያት ሊሸሽ ያልቻለውን ባላገሩንና ነጋዴውን ወይም ከዳተኛውን ቴዎድሮስን እንደሆነ ነው እንጂ የትግሬ ሹማምንት ባለፉት ዓመታት ወደ ሸዋ መጥተው በባደቄ በሽምብራ ኩሬ ከተላለቁት በቀር አሁን ደግሞ በተለይ የሠራዬው ሹም (ግዕዙ አቃጽነ ሠራዌ የሚለው) ተሰፋ ልዑል በግራኝ ጦር ላይ የሠራውን ዝብዱ ወደፊት እንመለከታለን ።

መቼም ግራኝ አህመድ ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዠምሮ በንጉሠ ነገሥቱና በጦር ሠራዊታቸው ላይ የሠራውን የማያውቅ አይኖርም ። እዚህ አሁን ከያጃቸው ድረስ ከመምጣቱ በፊት የትግሬዎቹ ሹማምንት እነ ጸሐፈ ላም ሮቤል በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ፤ የእንጎቱ ሹም ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ በአይፈርስ ፤ የጸሐፈ ላም ሮቤል ልጅ ዓምደ ሚካኤል በዝሆን ዱር ጦርነት በአማሮቹና በሸዎቹ ጐን እየተዋጉ መውደቃቸውን ያልሰማና የማያውቅ የትግሬ ተወላጅ አይገኝም ።

ስለዚህ አሁን ያን ሁሉ ያደረገው ግራኝ አህመድ በላስታና በአንጎት በኩል አድርጎ ወደ ሠራዊና ወደሺሬ ሲደርስ ልቡ የጨከነው መሣሪያውን እየያዘ ወደ ጫካ ወደ ተራራ ሲሰማራ የፈራው የቤተ ሰብ አባት ቤቱን ንብረቱን እርሻውን ላገሩ ለሃይማኖቱ ሲል ትቶ መሰደድ ወይም መሸሽ ያልፈለገው አሽናፊውን ተቀብሎ ግብሩን እየገበረ አሸናፊው የሚለውን እየፈጸመ መቀመጡ የታወቀ ስለሆነ በደፈናው "ወረደ ግራኝ እስከ ትግሬ . . . . . . . . ወተመጠውዎ ሲሬ ወሠራዌ" ያለው ትክክለኛ አይደለም ። እንኳን በዚያ በሩቁ ዘመን በቅርቡ በኢጣልያ ወረራ ጊዜ ሁሉ አርበኛ ሁሉ ስደተኛ መሆን ስለማይችል ከሕዝቡ ያውም አብዛኛው ተቸግሮ የኢጣልያ ተገዥ ነበር ። ግማሹም በባንዳነት እየተቀጠረ ወገኑን አርበኛ እስከ መውጋት ደርሷል ።

ግራኝ አህመድ ከላሊበላ ብዝበዛ በኋላ በዚህ ዓመት ፲፭፻፳፭ ዓ. ም. ሐምሌንና ነሐሴን እስከ መስከረም ድረስ የክረምቱን ወራት ወደ ትግሬ እያመራ በላስታና በአንጎት ግዛት በየመንገዱ ሠፈሩን እያደረገ ንጉሡ ወይም ለንጉሡና ላገሩ ሊከላከል ጦር ይዞ የሚጠባበቅ ሹም ያለበትን በያለበት ሰላይ እየላከ ሲያሰልልና ሲያስመረምር ከረመ ።

በዚሁ መሠረት በግራኝ ትእዛዝ የመድፈኞቹ ሹም ሻምሱ ለዋናው ግራኝ ላለ

(1) ወካዕበ በ፳ወ፮ ዓመተ መንግሥቱ ወረደ ግራኝ ውስተ ትግሬ በወርኃ ጥቅምት ወተመጠውዎ ሲሬ ወሠራዌ ። ንጉሥኒ ከረመ በደንቢያ ወተንሥአ እምሀየ በወርኃ ጥቅምት ወበጽሐ ወገራ ወኃለፈ እምሀየ በወርኃ ታኅሣሥ ወገብረ ፍኖተ እንተ ጸለምት ወበጽሐ አክሱም ወገብረ በሀየ በዓለ ጥምቀት ። ገጽ . . . . . 92 ።

በት ጦር ግምባር ቀደም ሆኖ ጦር ይዞ እየሰለለ ሲጓዝ ሐረር (1) ከሚባል ወንዝ አጠገብ የንጉሡ ያዔ ልብነ ድንግል የአባት ልጅ ያለችበት የክርስቲያኖችን ሠፈር እስላሞቹ አግኝተው ሁሉንም ማርከው ከነሴትዮዋ ወደ ግራኝ እንዳመጧቸው ግራኝም እርሷን በዕቁባትነት አስቀምጦ እንደወለደላት ፤ ሻምሱም ወደፊት ገፍቶ ቍጥራቸው የበዛ የክርስቲያን ጦር ሠራዊት አግኝቶ ተዋግቶ እንዳሸነፈና ከመካከላቸው ፩ሺ የእግረኛ ጦር ከፈጀ በኋላ ግማሾቹ ተማርከው የተረፉት እንደሸሹ የተማረኩትንም ክርስቲያኖቹ እስላሞቹን ማርከው ለማሠሪያ በያዙት ገመድ መልሶ እነሱኑ አሥሮበት ወደ ግራኝ እንዳመጣቸው ከመጡ በኋላ ግራኝ የምርኮኞቹን ጭንቅላት እንዳስቆረጠው የዓረቡ ጸሐፊ ያመለክታል (2) ።

ከዚሁ አያይዞ ግራኝ አህመድ ከላሊበላ ተጉዞ በቅዳ በኵል አልፎ ማህቁአ (3) በሠፈረበት ሰዓት ወዚር አዶሌ ከነጦሩ እንደደረሰለት ይገልጽና በዚሁ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል "እስላሞቹ ወደ ትግሬ ይጓዛሉ" የሚሉ ወሬ ስለሰሙ በአጠገባቸው ያለውን የትግሬን ጦር ለጦር አለቃቸው ለአዛዥ ደገልሃን ሰጥተው "ሂድና የማቱአህን መንገድ አንድም እስላም ወደ ትግሬ እንዳያልፍ ጠብቅ በሀበሻ አገር ከትግሬና ከቤገምድር በቀር የቀረን የለምና ይህ አገር የተያዘ እንደሆነ ከዚያ ወዲያ የምንሸሽበት ሥፍራ የለም" ብለውት ደገልሃን ጦር ይዞ የትግሬ መተላለፊያ የሆነውን የተራራ በር ለመጠበቅ መምጣቱን ይገልጻል ።

ንጉሠ ነገሥቱ በአሁኑ ሰዓት የሚገኙት እንደ ታሪክ ነገሥቱ በደንቢያ ነው ። ISIC ከዋሰል ጦርነት በኋላ ወደ ዐባይ መሸሻቸው የታወቀ ነውና ምናልባት ይኸን ትእዛዝ ለአዛዥ ደገልሃን ሲሰጡት ያሉት በጐጃም ግዛት ይሆናል ወይም በዚያን ጊዜ የግዛት ድልድል ደንቢያ ወደ ጐጃም እንደሆን አይታወቅም ። "ከቤገምድርና ከትግሬ በቀር የቀረን የለም" ያሉት ያሉበትን የጐጃም ግዛት ሳይቆጥሩ መሆኑ ነው ።

የሆነ ሆኖ አዛዥ ደገልሃን ጦር ይዞ ከመጣ በኋላ ግራኝም የአጐቱን ልጅ ዘሐርቡይ መሐመድን ጨምሮ በተራራው ሥር ተደብቀው የሚጠብቁትን ክርስቲያኖች ሳያይ ለውጊያ የሚመቸውን ሥፍራ ሲመረምር በጫካ ያሉት ክርስቲያኖች ውጊያ ገጠሙት ። እርሱና ጓደኞቹም ተዋግተው እነዚህን ክርስቲያኖቹን ወደ ተራራው መለሱዋቸው ፤ ቢሆንም ክርስቲያኖቹ በእስላሞቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ሲል ዓረብ ፋቂህ ያረጋግጣል ።

መቼም ግራኝን እግዚአብሔር በዚህ ዘመን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመቅጫ ስለመደበው አዳነው እንጂ በዚህ ቀን በተደረገው ውጊያ ሊሞት ይችል ነበር ። ነገር ግን በውጊያው ጊዜ አጠገቡ የነበረው ያጐቱ የመሐመድ ልጅ ዘሐርቡይ በመ

(1) እሪ እሪሪ ወይም ሐሮ እንደሆን ነው እንጂ በዚህ ክፍል ሐረር የሚባል ወንዝ መኖሩን አላውቅም ። ኮንቲ ሮሲኒ በዋግ ውስጥ እሪሪ የሚባል ሥፍራ መኖሩን ጽፈዋል ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 413 - 414

(3) ማቁት ወይስ መቋ በዋግና በዋጅራት መካከል የሚገኝ የዛሬው ኮረም ወይም የአላጌ በር ሳይሆን አይቀርም ። ነገር ግን ይህ ሥፍራ ገረገራ ከሚባለው ከዋድላ ግዛት መሆን አለበት ገራገራን የቡ ስንዮስ ዜና መዋዕል ዋድላና መቄት ከሚዋሰኑበት ላይ ያደርገዋል ምዕ. 62 ።

ርዛም ቀስት ሽንጡን በቀኝ በኩል ተመትቶ ሲሞት እርሱ ዳነ ።

በዚህ ቀን በቀስት ሽንጡን ተመትቶ የሞተው ዘሐርቡይ መሐመድ በሽም ብራ ኩሬ ጦርነት ጀውሂር ይባል የነበረውን ስልብ ከሁለቱ የንጉሥ አሳሳቾች (ሊቃነ መኳሶች) አንዱን መግደሉን አምባ ግሼን ፪ኛ የተከበበ ጊዜ ባንዱ በር በኩል ጦር ይዞ ሲዋጋ የዋለ ከዋነኞቹ የግራኝ የጦር አለቆች አንዱ መሆኑን እንባቢ ያስታውሳል ።

በዚህ ምክንያት በቀብሩ ጊዜ ከሁሉ ይበልጥ ያዘነው ግራኝ ስለ ዘሐርቡይ እሟሟት በማልቀስ ሰፊ ዲስኩር እንደ አደረገ የቀሩትም እንደዚሁ በየበኩላቸው ሲያዝኑ ሰምቶ ኤሚር ሑሴን "ከአገራችን ከወጣን ቀን ዠምሮ ሁል ጊዜ እንገድላለን የክርስቲያኖቹን አውራጃዎች ስንት ጊዜ ዘረፍን ስንት ክርስቲያን ነው እኛ የገደልነው ፤ በኛ ግን በዚህ ሰው ላይ በእድሉ የደረሰበትና የሞተብን ዛሬ ብቻ ነው ። የሚመሰገነውና የከበረው እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚፈልገውን (ሞትን ለዘሐርቡይ) ሰጠውና በሰማዕትነት ሞተ" ብሎ ያዘኑትን በማጽናናት እንደ ተናገረ ይገልጽና የዓረቡ ጸሐፊ በማግበቱ ግራኝ አህመድ የአጐቱን ልጅ ሞት ተዋግቶ ለመበቀል የጦር ሠራዊቱን ይዞ ወደ ተራራው ሲወጣ ክርስቲያኖቹ ከላይ የደንጊያ በትር ሲያወርዱባቸው እስላሞቹም በትሩን በጋሻቸው እየመከቱ ወደ ተራራው መድረሳቸውን ክርስቲያኖቹ እስላሞቹ እንደደረሱባቸው ባዩ ጊዜ ያሉበትን ለቀው ወደ ላይኛው ተራራ ተዛውረው እንደተቀመጡ ይጽፋል (1) ።

ክርስቲያኖቹ አሉበት ድረስ የግራኝን ደርሶ መዋጋት ወይም የማይመቸው ሆኖ ውጊያውን መተዉን ሳይገልጽ በዚህ ቦታ ላይ እንዳለ ሚስቱ ድል ወንበራ ወንድ ልጅ ወልዳለት ስሙ አህመድ ኢን - ነጋሺ መባሉንና በኋላ ግን ይኸው ልጁ በሠራዩ መሞቱን ይገልጻል (2) ።

የዚህን የተራራ ላይ ውጊያ ያውም ግራኝ በዘሐርቡይ ሞት ተናዶ ሊበቀል በሄደበት ሰዓት ዓረብ ፋቂህ ያልጻፈው ምናልባት ክርስቲያኖቹ ያሉበት በፍጹም ለፈረሰኛም ለእግረኛም ጦርነት የማይመች ስለሆነ ወይም በሚያውቁት መንገድ ክርስቲያኖቹ ወደኋላ ተመልሰው አምልጠውት ይሆናል ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 415 - 416

(2) አህመድ ኢን ነጋሺ ብሎ መሠየሙ በ፯ኛው መቶ ዓመት በነቢዩ በመሐመድ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በስደት መጥተው የነበሩትን ዓረቦች ተቀብሎ አስተናግዷል ብለው በሚያምኑበት በኢትዮጵያ ንጉሥ ስም መሠየሙ ነው ። ነገር ግን በዚህ ያረብኛ ስም የሚጠራ የኢትዮጵያ ንጉሥ በኛ ጽሑፍ አይገኝም ።

## ምዕራፍ ፹፩

## የእንደርታ የተምቤንና የአጋሜ ጦርነት (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. መስከረም - ጥቅምት) አህመድ አን - ነጋሽ ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ምክንያትና መቃብሩ ።

ግራኝ አህመድ የላሊበላን መቅደሶች ከዘረፈ በኋላ ወደ ትግሬ ጉዞውን ሲቀጥል በዚሁ በላስታ ሰሜን በመቄት ላይ በተለይ ዘሐርቡይ መሐመድ በመርዛም ቀስት ተመትቶ የሞተበትን ቀበሌ ዓረብ ፋቂህ ማህቁአህ ብሎታል ። ሥፍራውም በላስ ታና በትግሬ መገናኛ ተራራማና በሩ ለመከላከያ የሚመች መሆኑን ያወሳል ። መቄት ዛሬም ከላስታ የአውራጃ ግዛቶች አንዱ መሆኑ የታወቀ ነው ። ማህቁአህ ያለው በዚሁ ሥያሜ የሚጠራ መኖሩን አላውቅም ።

የሆነ ሆኖ የዓረቡ ጸሐፊ ዘሐርቡይ በሞተ ማግሥት የሟቹን ደም ለመበቀል ወደ ተራራው ሄደ ይልና የተራራውን ስም አይጠቅስም ። ነገር ግን በተራራው ሥር ጦርነት ተደርጎ ክርስቲያኖቹ የማርያም ቤተ ክርስቲያን ወዳለበት ወጥተው እንደሠፈሩ ይገልጽና በዚህ ጦርነት ጊዜ እስላሞቹ ሁሉ ተርበው የነበረውን ከዚያ አልፈው ቀርቀራ ሲደርሱ አገሩ ስንዴና ማር የመላበት ስለነበረ ረሃባቸውን በዚያ እንደተወጡ ያመለክታል ።

ዓፄ በእደ ማርያም (፲፬፻፷ - ፲፬፻፸ ዓ. ም.) ከሸዋ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ከዚያም ያን ጊዜ በአንጐት ስም ወደ ተጠቀለለው ወደላስታ የመጣ ጊዜ የአንጐት ሕዝብ ሴቱም ወንዱም በደስታ በእልልታ እንደተቀበለው በዚያም አንድ ከፍተኛ ሥፍራ ዓይቶ ደስ እንዳለውና በዚያ ላይ መቅደስ አሠርቶ መንበረ ማርያም እንዳሰ ኘው ከዚያ ወደ ዋዛንጌ አልፎ በቋርቋራ አደረ ብሎ ዜና መዋዕሉ ስለሚያረጋግጥ አሁን እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ ክርስቲያኖቹ በተራራው ግርጌ ተዋግተው ቀጥሎ የማርያም ቤተ ክርስቲያን ወደሚገኝበት ወደ ተራራው ወጥተው ተቀመጡ ያለው ይኸንኑ ነው (1) ። ስለዚህ በአሁን ጊዜ በላስታ አውራጃ ግዛት በመቄት የወረዳ ግዛት ውስጥ መኳት ማርያም ስለሚገኝ ዓረቡ ማህቁአህ ያለው በጊዜ ብዛት ዛሬ መኳት ተብሎ ይሆናል ። እንደዚሁም ቁራቁራ ማርያም የሚባል መኖሩ ቤተ ክህ ነት ባወጣው የአብያተ ክርስቲያን ዝርዝር ላይ በ፰፻፺ኛው ቍጥር ላይ የሚገኘው ስሙ ተመሳሳይ ነው ።

ግዕዙ ቋርቋራ ዓረብ ፋቂህ ቃርቃራ (ወይም ቀርቀራ) ያሁኑ ደግሞ ቁራቁራ ያለው በሌላ ጽሑፍ ላይ ገራገራ ተብሎ ይገኛል ። ዓረብ ፋቂህ ይኸንኑ ሥፍራ የት ግሬ የግዛት ክፍል ሲያደርገው የርሱን መጽሐፍ የተረጐሙት ሙሴ ረኔ ባሴት በማ ስታወሻ ከጨለቆት ደቡብ ምሥራቅ ከሰሐርት አጠገብ እንደሚገኝ ገልጸዋል (2) ከዚያ ወዲህ የተነሣው ያዔ ሱስንዮስ ጸሐፊ ትእዛዝ አዛዥ ተክለ ሥላሴ (ጢኖ) የን ጉሡን ጉዞ በተረከበት ላይ ከነፋስ መውጫ ጨጨሆ ከጨጨሆ ቀጥሎ ገረገራ እን

(1) ያፄ ዘርዓ ያዕቆብና ያፄ በእደ ማርያም ዜና መዋዕል ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 135 - 136

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 416 የረኔ ባሴት ማስታወሻ ቍጥር 2 ።

ደሚገኝ ገረገራም የመቋትና (የላስታ) የዋድላ ሕዝብ የሚዋሰኑበት ቀበሌ መሆኑን ይገልጻል (1) ።

እንግዲህ ግራኝ በወረረበት ሰዓት ገረገራ በሰሀርትና በጨለቆት አጠገብ የሚገኘው ሁሉ የዛሬው የወሎ ሰሜንና የአላጌ የማይጨው የዋጅራት የእንደርታ የሰለዋ አካባቢ ሁሉ በአንጐት ስም እየተጠራ ጠቅላይ ገዥውም በአይፈርስ ጦርነት የሞተው የአዝማች ተክለ ኢየሱስ ግዛት ነበር ። እርሱንም አንዱ ጽሑፍ የአንጐት ሹም ሲለው ሌላው ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ እንደሚለው ተገንዝበናል ። በሱስንዮስ ጊዜ ደግሞ ይኸ ሁሉ ቀበሌ በተለይ የላስታው መቂትና ገረገራ ሁሉ በጠቅላላው የአማራዎቹ ገዥዎች የነራስ የማነ ክርስቶስ ግዛት ይሆናል ። ባላባትና አገረ ገዥዎች በሚያስደስቱበት መጠን በድልድልና በሹመት ነገሥታቱ ወደፈቀዳቸው ይመድቡታል ። ነዋሪውም ከሦስቱ ወሰን ላይ ስለሚገኝ አገውኛ አማርኛና ትግርኛ ይናገር ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከላሊበላ በማቋአህ በኩል አድርጎ የአሸንጌን ሐይቅና የአላጌን በር ወደ ቀኝ ትቶ ከጦር አለቆቹ ውስጥ ወዚር ሙጋሂድን ወደ ሰሀርት (ወደቀኝ) ወዚር አዶሌን ወደ አበርጋሌ (ወደ ግራ) ልኮ እርሱ በመካከል በቀጥታ ወደ እንደርታ ሄዷል ማለት ነው ።

ዓረብ ፋቂህ ከዚሁ ከታሪኩ በማያያዝ ወደ አበርጋሌ አቅጣጫ የላከው ወዚር አዶሌ ከተመለሰ በኋላ ሠራዊቱን እንዲጠብቅ ለርሱ ትቶ የዘሐርቡይን ደም ለመበቀል ወደ እንደርታ ደርሶ ሀብቱን ዘርፎ ያለ ርኅራኄ ብዙ ሰው መፍጀቱ ከእንደርታ ደግሞ ወደ ተምቤን ሄዶ ከተምቤኑ ሹም ጋር ተጋጥሞ ፲ሺ ተዋጊ ወታደር እንደ ፈጀ ቀጥሎ በአጋሜ ራካት የሚባል ሹም የእግረኛና የፈረሰኛ ወታደር አዘጋጅቶ አገሩን ሊከላከል እስቧል ማለትን ቢሰማ በግሥጋሤ ወደ አጋሜ ሄዶ ሳለ ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው በነቢዩ መሐመድ ጊዜ በሽሽት የመጡትን ተቀብሎ ያስተናገደውን ንጉሥ በነርሱ አሳብና አጠራር ሰልሞ ስሙ አህመድ (እሻማት) ኤን ነጋሺ የሚባለው (የኢትዮጵያ ንጉሥ) የተቀበረበትን ቦታ መኖሩን እስላሞች ሰምተው ሄደን መቃብሩን እንጐብኝ ብለው ቢለምኑት የዘሐርቡይን ደም ባልገደሉት ሁሉ ላይ ለመበቀል የቸኰለው ግራኝ "ዛሬ የምንሠራውን የቁም ነገር ሥራ ጨርሰን መቃብሩ ነገ ይጐበኛል" ብሎ ጉዞውን በመቀጠል ሹም አጋሜ ተሰልፎ ከሚጠባበቅበት ከተራራማ ሥፍራ መድረሱን ያመለክታል ።

ዓረብ ፋቂህ ስለ እንደርታውም ስለተምቤኑም ጦርነት ብዙ ዝርዝር ሐተታ እንዳልጻፈ በዚህም በአጋሜ ስለሆነው ጦርነት የሚሰጠን ማስረጃ በጣም በአጭሩ ነው ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ። «እግረኛው የእስላም ጦር እፊት ቀደመና የቀስትና የደንጊያ በትር በየጋሻው ላይ እንደ ዝናም እየወረደበት እጠላት መካከል

(1) ወእምነፋስ መውጫኒ ኃበ ጨጨሆ ዘቀዲሙ ተፃብአ (ሱስንዮስ) ምስለ ንጉሥ ያዕቆብ ወሞተ ። ወእም ጨጨሆኒ ኃበ ገረገራ ውስተ ምድር ዘይትዋሰኑ ባቲ ሰብአ መቋት ወዋድላ ። የሱስንዮስ ዜና መዋዕል ገጽ 246 ።

ገብቶ ተዋግቶ በማሸነፍ ያባርር ጀመር ። የሚሸሹትንም ክርስቲያኖች የፈረሰኛ ጦር እስከ ተራራው አፋፍ ድረስ አባረራቸው ። ከዚያም ወዲያ እስከ ታች ድረስ ያለው ገደል ነበር ። ስለዚህ ሹም አጋሚ የእስላም የፈረሰኛ ወታደር እንደደረሰበት ባወቀ ጊዜ ወደ ገደሉ ተወርውሮ ክንዱን ከተሰበረ በኋላ አመለጠ» (1) ።

የዚህን የተምቤኑንም የእንደርታውንና የአጋሚውን ጦርነት ዓረብ ፋቂህ ባለ ፉት ዓመታት በአይፈርስ ፤ በባደቄ ፤ በዋስል ፤ በባሌ እንደተደረጉት ውጊያዎች የተዋጊን ወታደር ቍጥር የሟቹንና የገዳይን ስም እንደፊተኛው እየለየ የጦርነቱን ሁኔታ በማሟሟቅ አልጻፈውም ። ምክንያቱም ከውጊያው ዝቅተኝነት ይመስ ላል ። መቼም በአሁኑ ጊዜ የግራኝ የዘወትር አሸናፊነቱ ጭካኔው በያለበት ተስፋ ፍቶ ስለሚወራ ምንም እንኳን ትግሬዎቹ በሰላም ተቀብሎ አስተናግዶ መገበሩ የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ሆኖባቸው ለውጊያው ቢዘጋጁ ግራኝ መጣ ሲባል ያው ለውጊያ የተሰለፈው አብዛኛው የክርስቲያን ባላገር እንደገና መበርገጉና መፍራቱ ስለማይቀር ጥቂት እንደተቆራቈሰ የጦርነቱን ከባድነት የራሱን የግራኝን አዝማች ነት እያየ ተዋጊው በእርግጥ ዓረብ ፋቂህ እንደሚለው ብዙ ሳይመክት ሸሽቶ ይሆ ናል ። ደግሞም ዋናዋናዎቹ የትግሬ አዝማቾች ግማሾቹ ባለፉት ዓመታት በሸዋና በፈጠጋር በባደቄ ፤ በአይፈርስ ፤ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት እየተዋጉ ሞተው የቀሩ ትም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሆነው ባሁኑ ጊዜ የሚከላከለው ባላገርና የባላገር ቀንደኛ ይሆናል ። እነርሱም ጠቅሎ ሰብስቦ እየ[illegible]ባንድነት የሚያዋጋቸው በማጣት አብዛኛ ጊዜ ትንሽ እየተከላከሉ የሚሸሹት እንዚያው የክርስቲያን ባላገሮች ይሆ ናሉ ።

በአንድነትም ሆነው ቢገጥሙት ንጉሠ ነገሥቱ እነራስ እስላም ሰገድ ፤ እነ ራስ ወሰን ሰገድ ያልቻሉት የእስላም ጦር በአሁኑ ሰዓት አብዛኛው ነዋሪና ባላገር ለሆነው ጦር እንደማይበገር የታወቀ ነው ። እንዲያውም ባንድነት ሆነው ቢመክቱ ቍጥሩ በበረከተውና የጠራ መሣሪያ በያዘው ወታደሩ በቀላሉ ብዙውን ሕዝብ ለመፍጀት ይመቸው ነበር ። ስለዚህ ግራኝን ተቀብሎ ከመስለም በየአገራችን በተ ራራና በጫካ ሆነን እየተበታተንን በመከላከል እንሙት ብለው ራሳቸው የመከሩ በትና የወሰኑት ይመስላል ።

በዚህ ምዕራፍ ላይ ግራኝና ጦሩ ወደ አጋሚ ሲጓዙ በመንገድ አህመድ ኤን - ነጋሽ የሚባለውን በነቢዩ በመሐመድ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሆኖ ሲኖር የሞተ ውን መቃብሩን እንጐበኝ ማለታቸውን አንብበናል ። ነቢዩ መሐመድ በ፯ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ጣዖት ያመልኩ ከነበሩት ከሜካ ባላባቶች ጋር በተጣላና በተዋጋ ተሸንፎም ወደ መዲና ለመሸሽ በሚሰናዳበት ጊዜ (፮፻፳፱ ዓ. ም. እ. አው. ቍ.) ተከታዮቹን ሁሉ ከርሱ ጋር ይዞ ለመሄድ ስለቸገረው ያጐቱን ልጅ ጀፋርንና ወገኖ ቹን ወደ አበሻ አገር ሸሹ ፤ በዚያ አል ነጋሽ የሚባል ንጉሥ ፍርዱ የቀና በሰላም ሕዝቡን የሚገዛ . . . . . . እለና ወይርሱ ሂዱ ብሏቸው ፹፯ ወንዶች ፲፫ ሴቶች

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 417 - 420

ሆነው መምጣታቸው በየመጽሐፉ ተጽፏል (1) ።

እነዚህ የመሐመድ ወገኖች በመጡበት ጊዜ የነበረውን የኢትዮጵያውያን ንጉሥ ዓረብኛው ጽሑፍ አል ነጋሽ ይለዋል ። ነገር ግን የመጠሪያ ስሙን ባለመዉበቀ ምናልባት ንጉሥ የሚጠራበትን የነጋሢነት ስም "ነጋሽ" ብለውት ይሆናል እንጂ የመጠሪያው ስም ሊሆን አይችልም ። በዚህም በማናቸውም ዘመን አል ነጋሽ ወይም አል ነጋሢ የሚባል በኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን የተቀመጠ እስ ካሁን በታወቀው በየነገሥታት ዝርዝራችን ውስጥ የለም (2) ። ስለዚህ እነዚህ የመሐመድ ዘመዶች በመጡበት ጊዜ የነበረው አርማህ ፤ ወይም እለ ጸሐም እለዚያም እለ ገበዝ ስለሆነ እርሱን ወይም ከነዚህ አንዱን አል ነጋሺ ብለውታል ማለት ነው ።

ግራኝ አህመድ በትግሬ ግዛት ከገባ በኋላ ኃይለኛይቱ ሚሲቱ ድል ወንበራ የወለደችለትን ወንድ ልጅ በአህመድ ኢን ነጋሽ መሠየሙን ባለፈው ስላነበብን በዚህ በትግሬ አገር በተወለደው ልጁ ከዘጠኝ መቶ ዓመት በፊት የመሐመድን ወገኖች በመልካም ተቀብሎ አስተናግዷል ፤ እስልምናንም ተቀብሎ ነበር ብሎ ያመነበትን ንጉሥ ስያሜ ለወለደው ልጁ ለመስጠት እንደፈለገ ይታያል ። ነገር ግን እላይ እንዳመለከትነው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የእስላሞቹን ስደተኞች የተቀበለ ንጉሥ መኖሩ ምስክሩ ሲገኝ በዚህ ስም ያውም እስልምናን የተቀበለ ንጉሥ በፍጹም የለም ።

## ምዕራፍ ፹፪

የአክሱም ከተማና ሐውልት - የበሌው ነገድ ከግራኝ መተባበር — በአምባ ሠነይት አጠገብ በአርአዳ ግራኝ የፈጀው ሕዝብ (፲፭፻፳፯ ዓ.ም. ኅዳር - ታኅሣሥ)

ግራኝ አህመድ እንደርታን ፤ ተምቤንን ፤ አጋሜን ከመታ በኋላ ወደ አክሱም መጓዙን ለመግለጽ ዓረብ ፋቂህ ባጭሩ እንደዚህ ይላል "ከአጋሜ ተመልሶ ይማም ወደ አክሱም ለመሄድ አሰበ ። ይቺም ከተማ ጥንታዊ ናት ይባላል ። ያሠራት አይታወቅም እንዳንዶቹ ድዙ ኤል ቃርናይን ነው ይላሉ ፤ እውነተኛውን እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው ። በዚያም ቁመታቸው ፹ ክንድ ስፋታቸው ፲ ክንድ የሚሆን የደንጊያ ዓምዶች (ሐውልቶች) አሉበት ። አሁንም እንደቆሙ ይታያሉ" (3) ።

ዓረብ ፋቂህ አክሱምን የሠራት ድዙ ኤል ቃርናይን ነው ይላሉ ያለው ይኸን የመሰለ ስም በነገሥታት ዝርዝራችን የለም ። ብዙ ጊዜ በኛ ዝርዝር አብርሃ የሚለውን ሐውልቱ ኢዛና እንደሚለው በኛ ካሌብ የምንለውን ዓረቦች እለ አጽባሐ ስለ

(1) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ምዕ. 65 የሬኔ ባሴት ማስታወሻ በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ገጽ 419 ቁጥር 2 ።

(2) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ...... ምዕ 33 ገጽ 210 ተመልከት ።

(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 420

ሚሉት ይኸ ከላይ በዓረብኛ የተጠቀሰው ንጉሥ ስሙ በኛ ሌላ ይሆናል ።

አክሱም ብዙ ነገሥታት በየዘመኑ ብዙ ሕንፃና ሐውልት እየጨማመሩባት በየጊዜው ታንፃ ደመቀች እንጂ አንድ ንጉሥ ብቻውን ቆርቁሮ ያስፋፋት አይደለችም ። በየትም አገር ቢሆን አንድ ከተማ እየተሠራ የሚደምቀው በየጊዜው በሚነግሡ ነገሥታት ዘመን ነው ። አዲስ አበባን ዓፄ ምኒልክ ቆረቆሩ ፤ በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ብዙ ቤቶች ተሠሩበት ከዚያ በመጨረሻ ባፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እነሆ በጣም ከመድመቅ ላይ ይገኛል ።

ዓረብ ፋቂህ በዚህ ስሙ በማይገባንና በአመለከተው ንጉሥ አሠሪነት እርግጠኛ ስለአልነበረ "እውነተኛ ሠሪውን እግዚአብሔር ያውቃል" የሚል አወላዋይ ቃል መጨመሩ እውነት አለው ። እንደ ደንቡ ቆርቋሪውን ፤ ጀማሪውን አዳምቆ ሠሪውን ሊያውቅና ሊያመለክት የሚገባው የአገር ተወላጅ ጸሐፊ የተወው የጽሑፍ ቅርስ መሆን አለበት ። እርሱም ከወደ መዠመሪያው ደበሰበሰ ባለ አኳኋን እንደዚህ ሲል በግዕዝ ያመጣዋል "ክመዝአ ጥንተ ሡራሪሃ ለእምነ ጽዮን ገበዘ አክሱም ቀዲሙ ተሣረረት በመዝብር ኀበ ሀሎ መቃብሪሁ ለኢትዮጲስ ወልደ ኩሳ ወልደ ካም" ይላል ። በዚህ በመዝብር ያለውን አንዳንዱ ጽሑፍ በመዝሙር ብሎት ይገኛል (1) ። ይህ ሥፍራ በዚህ ስም በትግሬ ይኖር ይሆን ወይስ በፈራረሰ ሥፍራ ተቆረቆረ ወይስ ሥራው በመዝሙር ተወሰነ ማለቱ ይሆን አይታወቅም ፤ በዚህም ሥፍራ የካም የልጅ ልጅ የኩሳ (ኩስ) ልጅ የኢትዮጲስ መቃብር በአለበት ላይ መሆኑን ያመለክታል ። ይኸም ሴማውያን ሳይሆኑ የመዠመሪያዎቹ ቆርቋሪዎች የካም ወገኖች (ነገደ ካም) መሆናቸው ነው ። ሊሆንም ይችላል ። ከሴማውያን (ነገደ ዮቅጣን) በፊት ያገሩ ጌቶች የካም ነገዶች እንደነበሩ ታሪኩ ሁሉ ያመለክታል ።

ነገር ግን በአክሱምና በአክሱም ዙሪያ በመጠራ (ሠናፌ) በየሃ ባሉት ጥንታውያን ከተማዎች በሕንፃና በሐውልት ላይ የሚገኙት ጽሑፎች ራቅ ያሉት በሳባ ፊደልና ቋንቋ ቀረብ ያሉት በግዕዝ ነው የተጻፉት ። የግሪክ ሥልጣኔ በመካከለኛው ምሥራቅና በግብፅ በነፕቶሎሜ ገዥነት የተነሣ እስከ አክሱም መንግሥት ድረስ በመስማቱ በሳባውና በግዕዙ ጐን ጽርዑም (ግሪክኛ) እየተሰባጠረ ጣልቃ ገብቶ ይገኛል ። የካም ወገን የሆነው የኢትዮጵያ ወይም የርሱ ነገድ የተወው የሥልጣኔ ቅርስ በአክሱም ጐልቶ አለመታየቱ በማንም ዘንድ ታውቋል ። ይሁን እንጂ የሴምና የካም ዘር እንደሚደባለቅ ሥልጣኔና ቋንቋው ልማዱም መደባለቁ የማይቀር ነው ።

ሆኖም የአክሱም ሕዝብ በተለይ መሪ የሆነው ክፍል ከደቡብ ዓረብ ከሀበሳት ከሳባ ከሂሜያሪት እንደገባ የአክሱም ሥልጣኔ የነጋሢዎቹ ቋንቋና ጽሑፍ ሃይማኖታቸው ከደቡብ ዓረብ የመጣው የሳባውያን (የነገደ ዮቅጣን) መሆኑን መርማሪው ሁሉ ከተስማማበት ብዙ ዘመን አልፎታል ። ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ሐተታ ማድ

(1) Liber Axum-Conti Rossini ገጽ 3

ISIC

ረግ አስፈላጊ አይደለምና ግዕዙ ወደሚለው የአክሱም አመሠራረት እንመለስ ።

ከዚያው ከላይኛው ቃል አያይዞ ሁለተኛ ጊዜ በንግሥተ ሳባ ዘመን ይችው ንግሥት ያንን (የኢትዮጲስን) ከተማ ለውጣ ዓስባ በሚባል ሥፍራ መሥራቷን ሦስተኛ ጊዜ በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን መሠራቱን ለማመልከት እንደዚህ ብሎ ይጨርሳል "ወድኅሬሁ (ከኢትዮጲስ በኋላ ማለቱ ነው) ወለጠት ማክዳ (ንግሥተ ሳባ) ወሐንጸት በምድረ ዓስባ ወሣልስ ተሐንጸት በአብርሃ ወአጽብሐ . . . . ." (1) ።

ስለዚህ እንደ ግዕዙ ቃል አክሱም በነገደ ካም በኢትዮጲስ ተቆርቁሮ ባለ ከዚያ ደግሞ ንግሥተ ሳባ ከዚያ ራቅ ብላ የቆረቆረችውን በ፬ኛው መቶ ዓ. ም. ክርስትናን የተቀበለው ብዙ ታሪካዊ ሥራ የሠራው ብዙ ሐውልት ያሳነጸው አብርሃ (ዒዛና) ከነወንድሙ አክሱምን አድምቆ በመሥራት ገናና ከተማ አድርጎት ይሆናል ። የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጲስ አባሆሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ የሚባለው ንግሥተ ሳባ ምኒልክን ከሰሎሞን የወለደችው የሁለቱም አክሱምን መሥራታቸው ባገር ውስጥ ሲያያዝ የመጣ ጽሑፍ ሲተርከው ደንበኛ የደንጊያ ጽሑፍ ማስረጃ ይጐድለዋል እንጂ የነ አብርሃማ ሠሪነት ብዙ ሠነድና ማስረጃ በገንዘብና በሐውልቱ ላይ መልቷል ።

ዓረብ ፋቂህ በዚች ከተማ ቆመው የሚገኙት ሐውልቶች ቁመታቸው ፹ ክንድ ጐናቸው ፲ ክንድ ብሎ በዓይን ግምት የሰጠው መጠን ያንደኛው በሜትር በትክክል እየለኩ ከቆጠሩት ከነሊትማን ፤ ከነኮንቲ ሮሲኒ ምንም ያህል አልራቀም (2) ።

እነሱም እንደኛው ሐውልት ሥራው አስደናቂ በቁመቱም የየትም አገር ሀውልት የማይተካከለው ነው ፤ ካሉ በኋላ ቁመቱን ወደላይ 33 ሜትር ከ50 ስፋቱ ከግርጌ ባንዱ ማዕዘን 3 ሜትር ከዜሮ 4 በሌላው ማዕዘን 2.54 (3.04 — 2.54) አድርገው ከወደ ሜፉ እየጠበበ ከሄደበት ደግሞ ባንድ ወገኑ 2.35 በሌላው ወገን 1.68 (2.35 — 1.68) ስለሆነ ዓረብ ፋቂህ ከፍ ብሎ ከወደ ወገቡ ተመልክቶ ፲ ክንድ (ዙሪያውን 5 ሜትር) ያለው ከነዚያ ጋር የሚቀርብ ነው ። ቁመቱን 80 ክንድ (40 ሜትር) አድርጎ ከነዚያ ጋር (33 ከ50) የተለያየው በአሥር ሜትር ግድም ቢሆንም በዚህ በጦርነት ሰዓት በረጋ መንፈስ የረኸርም ቀን ጥናት ሳያደርግ አንድ ጊዜ ባየው ያይን ግምት ይህን ከውነት ያልራቀ መጠን በታሪኩ ጽሑፍ ላይ መስጠቱ አእምሮው የበሰለ ዓዋቂ መሆኑን ያስረዳል ። በትምህርት ረገድ በየመን በቤተ አል ፋቂህ ትምህርት ቤት ሕግና ፍርድ እየተማረ ያደገ በመሆኑ ስሙ ራሱ ዓረብ ፋቂህ ማለት "ሕግ አዋቂው ዓረብ" ማለት ነው (3) ።

(1) Liber-Axum ገጽ 3
(2) Storia d'Ethiopia-Conti-Rossini ገጽ 240 ። Deutsche Axum Expedition Inno Littmann D. Krencker BAND II.
(3) La litteratura etiopica-Enrico Cerulli ገጽ 120

ዓረብ ፋቂህ ባየው ጊዜ ይኸ ሐውልት እንደሌሎቹ ቆሞ እንደተመለከተው በጽሑፍ ያረጋግጣል ። ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒና ኢኖ ሊትማን በ፲፱፻ ዓ. ም. ላይ ይኸን ሐውልት ከባሻ ዮሐንስ ግቢ ወድቆ በሚያሳዝን አኳኋን ተሰባብሮ ነው ዓይተው የለኩትና የመረመሩት ። ምናልባት ግራኝ አህመድ ማናቸውንም የክርስቲያኖቹን መኩሪያ የሆነውን ሁሉ ሊፈርስ ሊቃጠል የሚችለውን ሁሉ ስለማይምር በርሱ ዘመን ፈርሶ እንደሆነ አይታወቅም ።

የዓረቡ ጸሐፊ ወደ ጦርነቱ ጉዳይ ተመልሶ የግራኝን ከአጋሜ ወደ አክሱም መጓዙን ከተረከበት ላይ ከአክሱሙ ሐውልት ጉዳይ ለጥቆ እንደዚህ ይላል "ይማም አር አዳህ (አርዓዳ ወይስ አራዳ) ላይ ሠፈረ ። አንዳንድ ያገሩ ነዋሪ ሕዝብ እየመጣ ተገናኘው ። መጥተው የተገናኙት በትግሬ የሚኖሩ የበለው ነገዶች ናቸው፤ እነሱም እስላሞች ናቸው ። ወደ አህመድ መጥተውም ክርስቲያኖቹ ሚስትና ልጆቻቸውን ሀብታቸውን ይዘው ተሰብስበው በዚህ ተራራ (አር አዳ) ላይ ይገኛሉ ። ወደነርሱም ለመድረስ ተንኮል ካልሠራህ በቀር አትችልም ብለው መከሩት ።"

እነዚህ የበለው ነገድ ስለሚላቸው ከዚህ በፊት በነአውራይ ኡስማንና በደብረ ሊባኖስ ቃጠሎ ምክንያት ጽፈናል ። የበለው ነገዶች ከግብጽ ደቡብ ጥንት ከአክሱም መንግሥት በፊት ዠምሮ መጥተው በትግሬ በሐማሴን በአከለ ጉዛይ በሠራዬ ገብተው የተቀመጡ ናቸው ። የመጡት ISIC ምድርን ጭምር ከወረረው ከበጅያ ሕዝብ ጋር ነው ። መጽሐፉ አንድ አንድ ጊዜ በለው ከለው ይላቸዋል ። የበለው ነገድ የሚባለው ከምጋሬህ እስከ ዳሮታይ ያለውን አገር ሲይዙ የከለው ደግሞ የሾተልን ወረዳ እንደያዙ ከከለው በፊት በዚህ ወረዳ የሮም ወገኖች እንደነበሩ ኮንቲ ሮሲኒ ያረጋግጣል (1) ።

እስልምና የተቀበሉበት ጊዜ በትክክል አይታወቅም ምናልባት በ፲ኛና በ፲፩ ኛው መቶ ዓ. ም. መካከል ወይም ከዚያ በፊት መሆኑን አላረጋገጥም ። ነገር ግን ባገር ላይ ካሉት የክርስቲያን ትግሬዎች ጋር በዘርም በሃይማኖትም ልዩነት ስላለ መቀመጥ እያቃታቸው ከነዚሁ በለው አብደላ የሚባለው በ፲፬ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ከትግሬ ወደ አዳል ሄዶ የሱልጣን ሰዓዲንን (መሐመድ አቡል በረከት ሰዓድ ዲን) ሴት ልጅ አግብቶ የርሱ ተወላጅ ሁሉ ወንዱ አውራይ (ዑራይ) ሴቷ ባቲ (ባቲያ) እንደሚባሉ በዚህ በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመን ባለው ጦርነት ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት በፊት ታማኝ ሆኖ ከግራኝ ጋር ይዋጋ የነበረው አውራይ ኡስማን የዚሁ ነገድ ተወላጅ መሆኑን በተረፈ የማኅፉዝ ልጅ የግራኝ ባለቤት ባቲያ ድል ወንበራ ፤ ኤሚር አቡበከር ቀጭኑ ሀብት ተቀብሎ ሊተወው የፈለገውን ደብረ ሊባኖስን ያቃጠለው አውራይ አቡበከር የበለው ነገድ መሆናቸውን ገልጸናል (2) ።

በዚህ ምክንያት ከሚስቱ ከባቲያ ድል ወንበራ ዠምሮ አሁንም ግራኝን እጅቦ ከአጋሜ ወደ አክሱም ከሚጓዘው ከሹማምንቱም ከወታደሩም ውስጥ ከአ

(1) Storia d'Etiopia Conti Rossini ገጽ 278

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 254 - 255

ዳል አገር የመጡ እሉባቸው ። በዚህ ጊዜ በአክሱም ዙሪያ በትግሬ ክርስቲያኖቹ እየፈሩ ሚስትና ልጆቻቸውን ሀብታቸውን ይዘው በየተራራው በየጫካው ሲደበቁ ያገር ተወላጅ የሆኑት ትግርኛም ደህና አድርገው የሚናገሩት የበለው ነገዶች ግራኝንና ጦሩን እንደወገናቸው በመቁጠር ከነዚያ እየተለዩ ወደ ግራኝ እየመጡ በሚያውቁት አገር መንገድ እየመሩ ከማስተናገድና ከመምከር ጋር ክርስቲያኖቹን አስወግተዋቸዋል.ማለት ነው ።

ግራኝ የነርሱን ምክር በጽሞና ከአዳመጠ በኋላ ስለውጊያው ያደረገውን የዓረቡ ጸሐፊ እንደዚህ ይላል «ይማም በዚያው በሠፈረበት አድሮ ሲነጋ ጦሩን ከሁለት ላይ ከፈለና እንዱን ክፍል ለአብድ ኢን ናስር ሰጠውና በቀኝ በኩል አድርገህ ወደ ተራራ ውጣ ብሎ አዘዘውና የቀረውን ርሱ ራሱ እየመራ በግራ በኩል ተጉዞ ገና ፀሐይ ሳትወጣ እተራራው ግርጌ ደርሰው ሁለቱም ወደተራራው መውጣት ዠመሩ ። ክርስቲያኖቹ ሁሉ እተራራው ጫፍ እጫካው ውስጥ ነበሩና እስላሞቹ ደርሰው ተዋግተው ያዙዋቸው ። የተማረኩትንም ይማም ጭንቅላታቸውን እያስቆረጠ ገደላቸው ። የቀሩትም የሚሸሹበት መንገድ አልነበራቸውም ነበርና እስላሞቹ ክርስቲያኖቹን በየጫካው በየሸለቆው በየጉድጓዱ እያገኙ ፈጁዋቸውና መሬቱ ሁሉ ሬሳ ለበሰ ። ሬሳ ከመብዛቱም የተነሣ መሄድ አልተቻለም ነበር ። እላይ እክርስቲያኖቹ ዘንድ የነበሩት እንደቆጠሩት ከነበሩት 10.550 ውስጥ አንድም ከሞት አላመለጠም ፤ እስላሞቹ የማረኩት የከብት መንጋና በግ ቍጥር የለውም ።

ISIC

ከዚህ በኋላ ይማም ወደ አምባ ሰነት (አምባ ሠነይት ?) መጣና ምርኮውን ሁሉ ወደ ሠፈር ለወዚር አዶሌ ልኮ በአምባ ሰነት እንዳለ አምሐ የሚባል የጦር አለቃ አዝማች ፋኒል (ፋኑኤል ?) ከተምቤን አገረ ገዥ ጋር በተምቤን ተሰብስበዋል ማለትን ስለሰማ ሌሊቱን በግሥጋሤ ሲሄድ አድሮ ሲነጋ ሁሉም እየጋለቡ ሀዛሩ (ሀስሮ ወይም ሀሳሮዋ ?) ከሚባል ከተማ ደረሱ» ይልና ዓረብ ፋቂህ ግራኝ ከተምቤኖቹ ጋር ሳይዋጋ ንጉሡን ፍለጋ ወደ አክሱም ተመልሶ መሄዱን ይገልጻል ።

ይማም በትግሬና በላስታ መካከል በመተላለፊያው በር ላይ ከአዛዥ ደገልሃን ጦር ጋር የተዋጋ ለት የአጐቱ ልጅ ዘሐርቡይ መሐመድ ስለሞተ በቀድሞው ጭካኔ ላይ አዲስ የጭካኔ መንፈስ ጨምሮ በዚህ ጊዜ በፊቱ ያገኘውን ሁሉ መከላከያ መሣሪያም ጠባቂም የሌለውን ሕዝብ ሴቱንም ሕፃኑንም ጭምር ያርዳል ማለት ነው ። ወደ ተራራም የወጣው ሕዝብ አብዛኛው ለሽሽት እንጂ ለመዋጋት አለመሆኑ የታወቀ ነው ። ግራኝ በዚያ ላይ ያገኘውን በመደዳው የተማረከውንም የተደበቀውንም ሁሉ በሙሉ ቍጥሩ 10.550 የሚሆን ሕዝብ በዚህ ቀን ብቻ አስፈጅቷል ማለት ነው ።

በዚህም ሥራው በመቁት (በላስታ) የሞተውን የዘሐርቡይን ደም ለመበቀል ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓይነት ምክንያት እያደረገ ክርስቲያናዊውን ሕዝብ በመፍጀት ባገሪቱ ላይ ለርሱ ታማኝ የሆነው የአዳልና የሱማሌ የዓረብ ዘር ከሚሰቱ ከድል ወንበራ ወገኖች ከበለው ነገድ ጋር ሆነው ባገሪቱ እንዲበረክቱ ፤ በዚህም የርሱና

የዘሩ እስላማዊ የገዥነት ሥልጣን እንዲጠነክር አስቦ ያደረገው ይሆናል ። ይኸን ንም የርሱን ፖለቲካ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ የሙሶሊኒ ኢጣልያኖች ለመከተል ፈትነው በተለይ ከለምለሙ አገር ኢትዮጵያውያኑን አጥፍተው የበረከተውን የነር ሱን ዘር ለመተካት ያለሙት ዓላማ ከግቡ ሳይደርስ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እነ ርሱን አስወግዶ እኛን እነበረ ሥፍራችን መለሰን ።

የ፲፮ኛው ዓመት የግራኝ አህመድ የ፳ኛው የሙሶሊኒ ወረራ ሙሶሊኒ እንደ ግራኝ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣቱ በወረራው ዘመን ማጠርና መርዘም ያኛው ከሩቅ ይኸኛው ከቅርብ መሆኑ ይለያያል እንጂ በተረፈ የወራሪነት ዓላማቸው እንደ ወራሪው ሁሉ ተመሳሳይ ነው ። ግራኝ ባንድ በዘሐርቡይ ሞት በሰበብ በአስ ባብ ቍጥሩ የበረከተ ሰው ሲፈጅ ኢጣልያኖች የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. ባንድ በግራሲያኒ ቁስለት ከዓርብ እስከ እሑድ ባሉት በ፫ ቀናት ውስጥ እስከ ፴ሺ ስላማዊ ሰው ፈጅተዋል ። በግራኝ ጊዜ የነበረውና በኢጣልያ ወረራ ዘመን የከዳተ ኛው ዝንባሌ ሃይማኖትንና ጐሣን በመለየት አንዱን ባንዱ ላይ ያመነውን ባላመ ነው ላይ እያስነሡ መሣሪያ እየሰጡ የማዋጋቱ ጠባይ ተመሳሳይ ነው ። የዘመን መራራቅ የመሣሪያ ዓይነት የሰውነት ቀለም ቢለያይም የሁለቱም ወረራ በተወረ ረው አገር ተመሥርቶ የመቀመጥ አንድ ዓይነት ምኞት ስለሆነ የሚለያይበት ምክ ንያት የለም ።


ISIC

## ምዕራፍ ፹፫

## የአክሱም ጽዮን ጽላተ ሙሴ - መከትር የመዘጋ ባላባት ከግራኝ ጋር ስለመደረቡ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ጥር - የካቲት)

ግራኝ በእንደርታና በአጋሜ ፤ በተምቤን ፤ በአክሱም ዙሪያ ባለፈው እንደተመለከ ትነው አገር ላገር እየዞረ በነዚህ ወረዳዎች እየሸሹ በጫካና በተራራ የተቀመጡትን ክርስቲያኖች ትግሬ በሚኖሩት በበለው ዘሮች እየተመራ ሰውን ሲፈጅ እንደ ታሪከ ነገሥቱ አነጋገር ንጉሡ የ፲፭፻፳፮ ዓ.ም ሕረትን ከረምት በደምቢያ (ቤገምድር) አሳ ልፈው ከዚያ በጥቅምት ወር ተነሥተው በወገራ በኩል አልፈው በጸለምት አድር ገው አክሱም ደርሰው የጥምቀትን በዓል እንዳከበሩ ከአክሱም ተመልሰው ወደ ጸገዴ ሲሄዱ ግራኝ እግር በእግር እርሳቸውን ሲከታተል እግረ መንገዱን የአባ ሳሙ ኤልን ገዳም አግኝቶ እንዳቃጠለውና በጥር ፳፫ ቀን (፲፭፻፳፯ ዓ.ም.) ወደ መዘጋ ሄዶ ከባላባቱ ከመከትር ጋር ተገናኝቶ በመከትር መሪነት ንጉሡን ለማሳደድ ወደ ደምቢያ መንዙን ንጉሡም ወደ ደራ ማምራታቸውን ይገልጻል (1) ።

(1) ንጉሥኒ ከረመ በደንቢያ ወተንሥአ እምህየ በወርኀ ጥቅምት ወበጽሐ ወገራ ወሐለፈ እምህየ በወርኀ ታኅሣሥ ወገብረ ፍኖተ እንተ ጸለምት ። ወበጽሐ አክሱም ወገብረ በህየ በዓለ ጥምቀት ወተመይጠ እምህየ ወገብረ ፍኖተ እንተ ጸገዴ ፤ ወግራኝኒ ተለዎ ድኅሬሁ ወአውዓያ ለመቅደሰ አባ ሳሙኤል አመ፳ወ፫ ለጥር ፤ ወኀለፈ እምህየ ወበጽሐ መዘጋ ፤ ወተራከበ ምስለ መከትር ወተ መጠውዎ ወመርሀዎ እስከ ደምቢያ ። ንጉሥኒ ገብረ እንተ ደራ ፤ ታ. ነገ. ገጽ 92 ። ባሴት ሬኔ ያሳ ተመው ገጽ 328 ፤



ከአክሱም ሐውልቶች በግማሽ የሚታዩት ።

ታሪከ ነገሥቱ የረኸምሙን ጉዞ የብዙውን ወራት ታሪክ እንደዚህ እየጠቃቀሰ ያለፈውን ያው የዓረቡ ጸሐፊ ከዚህ ሰፋ እያደረገ ያመጣዋል ። በእርሱም አጻጻፍ ግራኝ አህመድ እምባ ሠነይት በሠፈረበት ሰዓት አምሐና ፋኑኤል በተምቤን ጦር ይዘው ተሰብስበዋል ማለትን ሰምቶ ወደነሱ ለመድረስ ሌሊት ሲገሠግሥ ቀደም ብሎ እስላሞቹ ትግሬን ገብተው ዘረፉት የሚሉ ወሬ ቤጌምድር ውስጥ ለሚገኙት ንጉሥ ስለደረሳቸው ወደ አክሱም መሄዳቸውን በራሱ አነጋገር እንደዚህ ሲል ያመጣዋል ።

«የዚህን ወሬ (የትግሬን መበዝበዝ) ሰምቶ ያበሻው ንጉሥ ታላቅ ኀዘን ተሰምቶት ቀጥሩ የበረከተውን ጦሩንና የጦር አለቆቹን ይዞ ወደ አክሱም ሄዶ የአክሱሙን ትልቁን ጣዖት (ጽላተ ሙሴን) አስወጣ ። እርሱም ነጭ ደንጊያ ሆኖ በወርቅ የተሠራ ነው ። ከትልቅነቱም የተነሣ በሩ አላስወጣ ብሎ ቤተ ክርስቲያኑን ባንድ ወገን መቅደድ ግዴታ ሆነ ። ከዚያ አውጥተው አራት መቶ ሰው ተሸክሞት ሺሬ ውስጥ ታቦር ከሚባለው ምሽግ ተቀመጠ ።

ይማም በተምቤን ሆኖ ለጦርነት ምቹውን ሥፍራ (ከነአምሐ ለመዋጋት) ይዞ ሳለ አንድ አብደል ዋሀብ የሚባል አክሱም ከተማ የሚቀመጥ ዘሩ ከበለው ነገድ የሆነ ወደ ይማም መጣና የሀበሻ ንጉሥ አክሱም መጥቷል ብሎ ነገረው ። ከዚያ በይማም ትእዛዝ ጉዞው ተዠመረና በ፪ኛው ቀን እስላሞቹ አባ ገሪማ ደረሱ ። በዚህ ጊዜ . . . . . በ፫ ክፍል መሽገው ለውጊያ ከ[illegible]መጡት ውስጥ ሁለቱ ወርደው እንገብራለን ብለው ገቡ ፤ ይማምም ግብሩን ወሰነላቸው ። በሦስተኛው ቅጥር ሆነው እምቢ ብለው የመከቱትን ሄዶ ተዋግቶ አንድም ሳያስቀር ሁሉንም ፈጃቸው ።

ከዚህ በኋላ ለጦርነት ተዘጋጅተው ወደ አክሱም ጉዞው ሲቀጥል ማንም ሳይቋቋማቸው አክሱም ደረሱ ። በዚያ ሳለ በይማም ትእዛዝ . . . . . ያገሩን አንዳንድ ሰዎች ወታደሮቹ አምጥተው እፊቱ ባቀረቡለት ጊዜ ንጉሡ እዚህ ነበር አሁን ወዴት ሄደ ንገሩን ቢላቸው አንተ ከመምጣትህ ፯ ቀን በፊት መዘጋ ወደሚባለው አገር ከንጉሥ መከተር ዘንድ ሄዷል አሉት» (1) ።

ስለዚህ ገና ግራኝ በአጋሜ ጦርነት በነበረበት ሰዓት ንጉሡ ደንቢያ ሳሉ የግራኝንና የጦሩን ከትግሬ መግባት እንደሰሙ በኢትዮጵያ ወደ ተከበረችው እርሳቸውም በየጊዜው ርስትና ጉልት እየሰጡ ወደ አከበሩዋት ወደ አክሱም በግሥጋሤ በወገራና በጸለምት በኩል ሄደው ደርሰዋል ማለት ነው ። ወደዚያም የሄዱት የጥምቀት በዓልን ለማክበር ሳይሆን ስመ ጥሩዋን ጽላተ ሙሴን ከግራኝ ፊት ለማሸሽ መሆኑ ነው ። የጽላተ ሙሴን የደንጊያውን ነጭነት በወርቅ ማጌጧን ከትልቅነቷ የተነሣ በሩ አላስወጣ ብሎ ግድግዳ መቀደዱን የዓረቡ ጸሐፊ አመልክቶናል ።

ጽላተ ሙሴ ቀዳማዊ ምኒልክ አባቱን ሰሎሞንን ለማየት ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ ሊቀ ካህኑ ሳዶቅ እውነተኛዋን ጽላተ ሙሴን ሠርቆ ወደ አክሱም ይዞ መጥቶ በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ተቀምጣለች የሚለውን ያገራችንን የክብረ ነገ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 423 - 426

ሥትን ታሪክ ያልሰማ ወይም ያላነበበ የሚገኝ አይመስለኝም ። አሁን ዓረብ ፋቂህ ንጉሡ መጥተው ወደ ሺሬ ወስደው ሸሸጉት ብሎ በርሱ አጻጻፍ ትልቅ ጣዖት የሚለው በክርስቲያኖቹ ዘንድ የተከበረችውን ጽላተ ሙሴን መሆኑ ጥርጥር የለውም ።

ግራኝ ሞቶ ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡ ጊዜ ይህ ጽላት ከሺሬ ተመልሶ አክሱም ጽዮን መመለሱን ታሪክ ነገሥቱም ዓረብ ፋቂህም አይናገሩም ፤ ዓረብ ፋቂህ ጽሑፉን ከጣና ብዝበዛ በኋላ ሞቶ ይሁን ወይም ጽሑፉ ተቃጥሎ ይሁን ታሪኩን ስለ አቆመ ስለ ጽላተ ሙሴ በገላውዴዎስ ጊዜ የሆነውን ሊያውቅ አይችልም ።

ምናልባት ዓፄ ልብነ ድንግልን ከአክሱም እያሳደደ ወደ መዘጋ ከዚያም ወደ ደንቢያ ግራኝ ከሄደ በኋላ ፭ ዓመታት ያህል ባገሪቱ ላይ እስኪሞት ድረስ በግዛት ስለቆየ በነዚሁ በበለው ነገዶች ጠቋሚነት ደርሶበት ለኢትዮጵያውያኑ መኩሪያና አለኝታ የሆነችውን ጽላት ሰባብሯት እንደሆነ አይታወቅም ።

ይኸንንም የምናምንበት ምክንያት በ፲፰፻፷፰ ዓ. ም. እንግሊዞችና ዓፄ ቴዎድሮስ ጦርነት ሲገጥሙ ሲሉ እናስታርቃለን ብለው ከኢየሩሳሌም የመጡት ኢጲስ ቆጶሱ ይስሐቅና ቄሱ ጢሞቴዎስ ባፄ ዮሐንስ (ያን ጊዜ ደጃች ካሣ) ፈቃድ ጽላተ ሙሴን ለማየት ገብተው ቀሳውስቱ ያቀረቡላቸው መጠኑ ከዚህ በጣም ያነሰ በወርቅም ያላጌጠ መሆኑን ፲ቱ ቃላት ካለበት ከሙሴ ጽላት ጋር በፍጹም የማይመሳሰል መሆኑን በጽሑፍ ዘርዝሮ ሥዕሉንም አንሥቶ ወዳገሩ ሲመለስ ጢሞቴዎስ በአሳተመው መጽሐፍ ላይ[illegible]ጽታል (1) ።

በተረፈ ግራኝ አህመድ አክሱም በሠፈረበት ሰዓት የከተማ ነዋሪዎቹ ከመድረስህ ከ፭ ቀን በፊት ንጉሡ ወደ መዘጋ ሄዷል ብለው እንደነገሩት ወዲያው ተከታትሎ ከዚሁ ከመዘጋ ባላባት ከመከትር ዘንድ ክርስቲያኖቹ ወደኔ ይጓዛሉና ሳይገድሉኝ ድረስልኝ የሚል ደብዳቤ የያዘ መልእክተኛ ወደ ግራኝ ደርሶት ሁሉንም ትቶ መከትርን ለመርዳት ከአክሱም በሺሬ በኩል አድርጎ ወደ መዘጋ መገሥገሡን የዓረቡ ጸሐፊ ያረጋግጣል ። ከዚሁ እያይዞ ሲጓዝ ውሎ ማታ ደብረ ዓባይ ከሚባለው ከአባ ሳሙኤል ገዳም ደርሶ በዚያ መስፈሩን ፤ ገዳሙ በብዙ ቀለም (ሥዕል) ያጌጠና አስደናቂ መሆኑን ፤ በገዳሙ ውስጥ መነኮሳቱ ተሰብስበው እንዳሉ እንደ በግ ታርደው ደማቸው በቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ መፍሰሱን የሟቾቹ መነኮሳት ቍጥር ፷፻ መሆኑን ያስረዳል (2) ።

ይህ የአባ ሳሙኤል ገዳም የሚገኘው በዛሬው የአገዛዝ ድልድል በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በሺሬ አውራጃ በቆራሮው የወረዳ ግዛት ውስጥ ነው ። ቤተ ክህነት ባወጣው የቤተ ክርስቲያን ዝርዝር ውሳጥ ፲፱፻፹፩ኛ ቍጥር ተሰጥቶት የተተከለበት ዘመን ፲፫፻ ፲፰ ዓ. ም. መሆኑ ተመልክቷል ። ተካዩ አልተመለከተም ። ነገር ግን ባመተ ምሕረቱ ሲታሰብ ዘመኑ ያፄ ዳዊት ቀዳማዊ ይሆናል ። እርሳቸውም የገዙበት ዘመን ከ፲፫፻፹፭ እስከ ፲፬፻፬ ዓ. ም. ነው ። አባ ሳሙኤል ዘቈየፃና አባ ሳሙ

(1) Deux ans de Séjour en Abissinie Dimotheos ምዕ. 10 ገጽ 125 - 144
(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 428

ኤል ዘደብረ ዓባይ የተተከሉበት ዘመኑ አንድ ስለሆነ ፣ የሁለቱም ተካይ በእርግጥ ዓፄ ዳዊት ይሆናሉ ። ዓፄ ዳዊት ለአባ ሳሙኤል ዘቁየፃ መተዳደሪያ የጕለቱበት ዕጣን ዞሬ ፣ ደንበላቢላ ማይ ዳማስ . . . . . እያለ ገበዘ አክሱም ሲጠቅስ ለደብረ ዓባይ አባ ሳሙኤል ደግሞ ልጃቸው ዓፄ ይስሐቅ በሺሬ ጣጣ ምላጣ ደምቤ ሐክፈን የሚባሉትን ሌላም መሬት ጉልት አድርገው መስጠታቸው ተመልክቷል (1) ።

ግራኝ ከሺሬ በዋልድባ በወልቃኢት በረሀ ሲጓዝ ሠራዊቱ በረሀብና በጥም በጉዞም እየደከመ በብዙ ችግር ወደ መከትር ግዛት ደረሰ ። ከሠራዊቱም ብዛት የተነሣ አቧራው ቆሞ በሩቅ ለባላባቱ ለመከተር ስለታየው እስኪ ምን ይሆን ሄዳችሁ መርምሩ ብሎ የላካቸው ፈረሰኞች መጥተው ከግራኝ ተገናኙ ፣ ግራኝም አይዞህ ደርሰንልሃል ብላችሁ ለጌታችሁ ንገሩት ብሎ መልሶ ወደ መከተር ላካቸውና ጉዞውን ይቀጥል ዠመር ።

በዚህ መካከል የመከትር ጦር ካፄ ልብነ ድንግል ጦር ተዋግቶ ተሸንፎ ራሱ መከተርም ተከቦ ተቸግሮ ኖሮ የግራኝን መምጣት ሲሰማ ምንም አሞት ቢሰነብት ተነሥቶ ኮቱን ለብሶ እፈረሱ ላይ ወጥቶ በ፲፭ሺ. የኑብያ ጦር ታጅቦ መጥቶ ከግራኝ ጋር በደስታ ተገናኘ ። ግራኝንም ከነጦሩ አሥር ቀን ሙሉ በአገሩ ላይ እንደሚገባ አስተናግዶ ሴት ልጁንም ዳረለት ሲል ዓረብ ፋቂህ ይገልጻል (2) ።

ይህ መከትር የሚባለው የመዘጋ ባ፲፩፻ቹ ሃይማኖቱ እስላም ነው ። ስሙም በአጠራር ተለዋውጦ መከትር የተባለው ከመሠረቱ ዓረብኛ ስሙ ሙክታር ሳይሆን አይቀርም ። መዘጋ ዛሬ ጋላባት በሚባለው በኢትዮጵያና በሱዳን ወሰን መካከል የሚገኝ የአትባራና የሲናር በዚያ አካባቢ ያለው የአውራጃ ግዛት ነው ። እንዳንድ ጊዜ ራስ ኤል ፊል ይባላል ። ግዛቱ በየጊዜው እየሰፋም እየጠበበም የሄደበት ጊዜ አለ ። የዛሬ ከተማው መተማ ነው ። በውስጡ የሚገኘው ሕዝብ ከቀድሞ ከኑብያ ፣ ከመርዌ የወረደ እንደዚሁም ከበጀያ የመጣው የበለው ነገድ ቅልቅል ነው ። ሃይማኖቱ ጥንት እንደበጅያ እንደበለው ነገድ አረመኔ መሆን አለበት ። በኋላ ግን ኑብያ እንደ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትን በያዘበት ጊዜ ከነዚህም ውስጥ ሁሉም ባይሆን አንዱ ክፍል ክርስትናን ይዞ የቆየ ሳይሆን አይቀርም ።

ነገር ግን የግብፅ ጦር ከሰሜን እየመጣ ከ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ የኑብያን ክርስቲያኖች ሲያጠቃ ግብፆችና ዓረቦችም እየገቡ እየሰበኩ በየጊዜው በጦርም በስብከትም የኑብያን ክርስቲያኖች እያሰለሙ ሲያመነምኑዋቸው ቆይተው በመጨረሻም የግብጽ ጦር ኑብያ መጥቶ እስላሞቹን ረድቶ ሥልጣን ስለአስያዛቸው

(1) በእኩቴተ እብ . . . . ጐለትኩ እነ ሐፄ ዳዊት ለአቡየ ሳሙኤል ዘቁየፃ ዕጣን ዞሬ ደንበላቢላ . . . ። ጐለትኩ ጕልተ እነ ንጉሥ ይስሐቅ በምድረ ሲሬ ለአቡነ ሳሙኤል ዘደብር ዓባይ ጣጣ ምላጣ ደምቤ ሐክፈን አድ ሰሙር ዓድ ቀልቀል እምባ ፅዕድ . . . . . ገበዘ አክሱም ኮ. ሮሲኒ ያሳተመው ገጽ 22 - 23 ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 426 - 431

ከ፲፫፻፳፫ ዓ. ም. ዠምሮ የኑብያ መንግሥትና ሕዝብ ጨርሶ የእስላም መንግሥት ሆነ (1) ።

ስለዚህ ምናልባት በዚሁ በ፲፩ኛው መቶ ዓ. ም. መዠመሪያ ላይ የኑብያ ምሥራቃዊው ክፍል የሰናርና የጋላባት ሕዝብ የበለው ነገድ እስልምናን ሲቀበል የመዘጋ ሕዝብም አብሮ ተቀብሎ ይሆናል ። እንደ ኤው. ቍ. ፲፯፻፷፪ - ፲፯፻፷፭ ዓ.ም. መካከል በኢትዮጵያ የነበረው ጀምስ ብሩስ ባዔ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ፈቃድ ባገሩ ተቀምጦ ወረዳውን በጐበኘበት ሰዓት መላው የመዘጋ ሕዝብ እስላም መሆኑን ግዛቱም ከደጃች ነጮና ከወይዘሮ አስቴር ለተወለደው ለአቤቶ ክንፉ በወጣትነቱ ሰዓት በራስ ስሑል ሚካኤል ፈቃድ ተሰጥቶት እንደነበረ ራሱ ብሩስ ከብላቴን ጌታ አሞንዮስ ጋር ዓይቶት እንደነበረ የፊተኛው ሹም አብደል ጀሊል ይባል እንደ ነበረ ይገልጻል (2) ።

የሆነ ሆኖ የመዘጋ ባላባት ባለፈው እንዳነበብነው እንደ ሐድያ ባላባት በውስጥ አስተዳደሩ ራሱን ችሎ ለኢትዮጵያ ነገሥታት እነርሱ ደከም ሲሉ ለግብጾች ወይም ለሁለቱም ባንድ ዘመን እየገበረ የተቀመጠ ሕዝብ ነው ። ባላባቱ በኛ በኩል አንድ አንድ ጊዜ ንጉሠ መዘጋ "የመዘጋ ንጉሥ" አንድ አንድ ጊዜ ሥዩመ መዘጋ "የመዘጋ ሹም" ሲባል ባረቦቹና በእስላሞቹ በኩል የመዘጋ ሱልጣን ይሉታል ። ነጋሪትም እንዲያስመታ ተፈቅዶለታል (3) ።

ስለዚህ ባለፈው በደቡቡ ኢትዮጵያ ክፍል የደዋሮ ፤ የሐድያ ሕዝብና ባላባት በሰሜን በኩል በተምቤንና በአክሱም የበለው ነገዶች እንዳደረጉት አምነው ሲገብሩለት የነበረውን ንጉሠ ነገሥት አሁን በሃይማኖት የሚመስላቸው የግራኝ ጦር ሲመጣ እየከዱ ግራኝን በደስታ ተቀብለው እንዳስተናገዱት ፤ በሰላም መንገድ በመምራትም እንዳገለገሉት ይህ የመዘጋ ባላባትና ሕዝብም ባሁኑ ጊዜ ይኸንኑ መስመር ተከትለዋል ማለት ነው ።

ታሪከ ነገሥቱ በጥር ፳፫ ቀን ግራኝ የአባ ሳሙኤልን ገዳም አቃጥሎ ከዚያ አልፎ መዘጋ ደርሶ ከመከትር መገናኘቱን መከትርም በደህና ተቀብሎ አስተናግዶ ንጉሡን ለማባረር እስከ ደንቢያ ድረስ መምራቱን ባለፈው አመልክቷል ።

እንግዲህ ዓፄ ልብነ ድንግል በጥር ፲፩ ቀን የጥምቀት በዓልን አክሱም አክብረው በቶሎ ግራኝ ሳይደርስባቸው ሺሬን አልፈው ወደ መዘጋ ሲሄዱ ግራኝ በ፲፪ኛው ቀን በጥር ፳፫ ቀን ሺሬ ደርሶ የታወቀውን የአባ ሳሙኤልን ገዳም አቃጥሎ በዚያ የነበሩትን ፳፪ መነኮሳት እንደ በግ አሳርዶ ጉዞውን ወደ መዘጋ ቀጥሏል ። ከርሱ ቀድመው የሄዱት ዓፄ ልብነ ድንግል በመዘጋ ሲያልፉ መከትር እንደ ጥንት ልማዱ ተቀብሎ በማስተናገድ ፈንታ የግራኝን ከ፺ ዓመት ዠምሮ አሸናፊነቱን አሁን ደግሞ ትግሬ በተለይ አክሱም መግባቱን ስለሰማ ለተሸነፉት ንጉሥ ግብ

(1) Storia della Nubia Cristiana-Ugo Mouneret devillard ምዕ. 22 ፣ ገጽ 220 - 223
(2) ጀምስ ብሩስ በሙሴ ካስቴራ ትርጉም ቮሊዩም ፫ ገጽ 408 - 412
(3) Chronica de susenyos ገጽ 162 ። ሪኔ ባሴት በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ገጽ 425 - 426 ማስታወሻ ቍ. 1 ።

ርም አልገብር ስንቅም አልሰጥ ብሎ በዚሁ የክርስቲያኑ ጦር ተናዶ ስለወጋውና ስለአስቸገረው ድረስልኝ ብሎ ወደ ግራኝ ልኮ ግራኝም ወደርሱ ሲጠጋ እንደታመመ ከደስታው ብዛት የተነሣ ከተኛበት ተነሥቶ የጦር ልብሱን ለብሶ በግራኝ ጉን ተሰልፏል ማለት ነው ።

ስለዚህ ግራኝ በፊት ከአዳል ፣ ከሱማሌ ፣ ከደቡቡ ክፍል ከሰበሰበውና ከደረጀው ጦሩ ጋር በአሁኑ ሰዓት ያገር ተወላጅ የሆነውን በትግሬም በመዘጋም የሚገኘውን ነዋሪውን የበለውን ነገድ ስላስከተለ ሞት እስኪገላግላቸው ድረስ ወደፊት ያለው የ፲ ዓመታት ጊዜ ላዩ ልብነ ድንግል ካለፈው የበለጠ ምን ያህል እንደሚከብድ ወደፊት እናነባለን ።

ከሥር ትንቢት ተንተርሶ የተነሣው የግራኝ ዋና ዓላማው የክርስቲያኑን ጦር መደምሰስ የሚጸልይበትን ገዳምና ቤተ ክርስቲያን አመድ ማድረግ ሕዝቡን ማስለም ከመሆኑ ጋር እንደዚሁም በፖለቲካ ጋብቻ አገሪቱን ለመግዛት ዋና ምኞቱ ስለሆነ የሹማምንትን የመኳንንትን ሚስቶች ለራሱ ሹማምንት እንደ ዕቃ እያደለ ከንጉሡ ነገሥቱ ወይም እንደሐድያ እንደ መዘጋ ካሉት የባላባት ልጆች ጋር ይጋባል ወይም ትወልዳለች የተባለችውን በቶሎ የራሱ እቁባት ያደርጋል ።

ይኸም በዚያን ዘመን በተለይ በምሥራቃዊ ሕዝብ ገዥዎች ዘንድ የተለመደ ነበር ። ይኸን ፖለቲካ ከዓፄ ልብነ ድንግል በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ እንደተከተሉት አንብበናል ። በቅርቡ [illegible]ሸዋ የሣህለ ሥላሴ ዘር በርከቶ እንደኛው የዘር ግንድ ሲደከም እንደኛው የሚነሣበት ምክንያት ከብዙ ዕቁባት መውለዳቸው መሆኑ ትዝ ይለናል ። በዚህም ዓይነት ከብዙ የባላባት ሴት ልጆች የተባዙ ትውልድ ለማትረፍ የታደሉት ሣህለ ሥላሴ የዛሬው ንጉሠ ነገሥት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘር ግንድ የመሆናቸው ደንብ በሕገ መንግሥት ጸድቋል ።

ስለዚህ ግራኝ ጦርነቱን ከጀመረበት ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ እስካሁን ድረስ በታወቀችው ሚስቱ በድል ወንበራ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ወረራውን ከጀመረ አንሥቶ ፤

፩ኛ. ከባሌ (ቃጅማ) የተማረከችውን የተክለ ሃይማኖትን ሚስት በአይበስ ለሐፄ በኩል ከንጉሡ የምትዛመደዋን ስሟን ሂጅራህ አሰኝቶ ፤

፪ኛ. የሐድያውን ባላባት ልጅ ከሦስት ወር በኋላ የሞተችውን ፤

፫ኛ. በቅርብ ጊዜ ከአንጎት የተማረከችውን የንጉሡን የእህት ልጅ ፤

፬ኛ. አሁን ደግሞ የሱልጣን መከተርን ልጅ አግብቶ ሚስትም ዕቁባትም እንዲበዛለት ማድረጉ በርሱ ምኞትና የሩቅ ዓላማ ከነገሥታቱና ከየባላባቱ ዘር ተዋልዶ በየአውራጃው ባላባትነት ውስጥ የርሱ ዘር እንዲተካ ከነዚሁ መካከል የሚመጥነውና የተመረጠው ልጁ በኢትዮጵያ እንዲነግሥ ነው ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልተጨመረበት ብዙ ቢያስቡም ከብዙው አንዱም ላይከናወን ፤ ብዙ ቢወልዱም ከብዙው አንዱም ላይባረክ ይችላል ። አንዳንድ ጊዜ የየዋህ ባላገር ልጆች የዕውቀትና የማስተዳደር ጸጋ አግኝተው ከቁም ነገር ሲደርሱ የታላላቅ ኃያላን ነገሥታትና መሣፍንት ልጆች ንዝሕላል ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህ እግዚአብሔር ከኃያላን ችሎት ከአዋቂዎች አእምሮ እየሠወረ የራሱን ምሥጢራዊ ሥልጣን የሚገልጽበት በሀብት ብዛት በሰው ልጅ እውቀት የማይጨበጥ ልዩ መለኮታዊ ፈቃድ ነው ።

ግራኝም እነዚህን ሁሉ ቢያገባም ከነዚህ ሁሉ ከተወለደው አንዱም በርሱ እግር ተተክቶ ኢትዮጵያን እንደርሱ ለመግዛት ቀርቶ የተነሣ በፍጹም የለም ። ከሞተ በኋላ እንኳን በኢትዮጵያ ዙፋን በገዛ ወገኖቹ በሐረርጌ እንኳ የርሱ የቀጥታ ተወላጆች አቅም አንሷቸው በሐረርጌ የርሱን ሚስት ድል ወንበራን አግብቶ በሱልጣኖቹ አልጋ የተተካው ኑር የሚባለው የወዚር ሙጃሂድ ልጅ ነው ።

ከየትኛዋ ሴት የተወለደው መሆኑን ሳይለዩ ሊቁ ኤንሪኮ ቼሩሊ የግራኝ ወገኖች የአባታቸውን የግራኝን ሥያሜ ይማም የሚባለውን የማዕርግ ስም ይዘው ላሜር ጊዜ ከሌሎች ኤሚሮች ጋር እየተሰባጠሩ እንደ አውሳ ቀጥር (ከ፲፭፻፴፯ እስከ ፲፭፻፶ ዓ. ም.) በአውሳ መግዛታቸውን ብቻ ያመለክታሉ (1) ። ይኸም እንደ ጨረፍታ ታይቶ ከ፳፫ ዓመት በኋላ የጠፉ ነው ማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፹፬

ግራኝ አህመድ ንጉሡን ለመማረክ ከመዘጋ በጸለምትና በደምቢያ አድርጎ ወደ ጐጃም እንደገሠገሠ - ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ዓባይ ዳር ሊማረኩ ሲሉ ለጥቂት በፈረስ አምልጠው እንደሄዱ (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. የካቲት ፳፱ ቀን) ከግዕዝና ከአማርኛ የተቀየጠ የዘመኑ ቋንቋ ።

ISIC

ዛሬ በሰለጠነው ዘመን በሰለጠኑት አገሮች በጦር ግምባር ነገሥታት ቢሞቱ ልጆቻቸውን ፣ የጦር አለቆች ቢወድቁ ምክትሎቻቸውን መሪ አድርጎ ለውጊያ የቀረበው ወታደር ከነሹማምንቱ ጠላቱን ይመክታል ። ስመ ጥሩ ንጉሥ ወይም አለቃ ከሞተ በኋላ በሚቹ ምትክ የተተኩ መሪዎች በብዙ የጦርነት ግንባር ጦርነቱን ቀጥለው ድልን በጠላቶቻቸው ላይ እያገኙ አገራቸውን ከመገዛት ያዳኑ ወይም የሰው አገር የገዙ ሞልተዋል ። ሌሎች በተለይም በሥልጣኔ ወደኋላ የቀሩ አገሮች ወታደሮች የታወቀ ስመ ጥሩ ንጉሣቸው ወይም የጦር መሪያቸው ተዋግቶ በጠላቱ እጅ ሲሞት ወይም ሲማረክ ወታደሩ ተስፋ በመቁረጥ በተተኪውም ላይ እምነት በማጣት የደረጀው ጦር እንደሚገባው ሳይዋጋ በመሪው ሞት ብቻ ተሸብሮ የሚሸሽ ፣ በመሸሹም ራሱንም አገሩንም በባርነት ለወራሪ የሚሰጥ ሞልቷል ። የዚህም ሁኔታ ከዛሬ ዘመን ይበልጥ ከጥንት ዠምሮ ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን አልተሻሻለም ። ግራኝ ሞተ ተብሎ የተወራ ጊዜ አዶሌ «ይማም ቢሞት አንድ ሰው ሞተ ማለት ነው ፣ ጦርነቱን ለመቀጠል እኛው እንበቃለን» ያለው በእስላሞቹ በኩል ያለውን ግማሽ መሻሻል ከግማሽ መግደርደር ጋር ያሳያል ።

(1) Studi Etiopici-I-La Lingua e la Storia di Harar ገጽ 38

ስለዚህ ግራኝ አህመድ የዚህን መንገድ ደህና አድርጎ ያውቀው ስለነበረ ንጉሡን ለመማረክ አጥብቆ ይፈልግ እንደነበረ የታወቀ ነው ። ከሁሉ ይበልጥ በዚህ ባሁኑ ምዕራፍ በስንት ድካም በእንዴት ያለ ብልሃትና ጥረት ንጉሡን ሊይዛቸው ሲሞክር በእንዴት ያለ ሁኔታ ከደረሰባቸው በኋላ እንዳመለጡ እንመለከታለን ።

በዚህ በደምቢያና በዓባይ ዳር ግራኝ ንጉሡን ለመያዝ ያደረገውን ሙከራ ስለ ዚህም የፈጸመውን ጦርነት ታሪከ ነገሥታችን ይጠቅሰዋል ። በፊት የመዘጋ ጉዞውን አመጀመሪ ለጥር ወኀለፊ (ግራኝ) እምሀየ ወበጽሐ መዘጎ ወተራከበ ምስለ መከትር ወተመጠውዎ ወመርሀዎ እስከ ደምቢያ" ካለ በኋላ አሁን ደግሞ ረዥሙን የደራ ጉዞና የዓባይ ዳሩን ጦርነት እንደዚህ ብሎ ያልፈዋል «ንጉሡ ወደ ደራ ሄዱ ። መለሳይም ከኋላ ተከታትሎ በዓባይ ዳር በየካቲት ፳፪ ቀን ተገናኙ (ተዋጉ) ። በዚህ ቀን ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ልጁ ብእሴ እግዚአብሔር ቀኝ ጌታ ወሰንጌና ብዙዎች ሞቱ ቍጥር የሌለው ገንዘብ ጠፋ የተማረኩም አሉ» (1) ።

ይህ ቃል ግራኝ የአባ ሳሙኤልን ገዳም ካቃጠለ በኋላ በጥር ፳፫ ቀን ከዚያ አልፎ ወደ መዘጋ መጥቶ ከዚህ በፊት እንዳልነው ከሱልጣን መከትር መገናኘቱን ፤ መከትርም ተቀብሎ ካስተናገደው በኋላ እስከ ደምቢያ ድረስ እንደሸኘው ከጠቀሰ በኋላ አሁን ደግሞ ንጉሡ በዚህ ጊዜ ከደምቢያ ወደደራ እንደሄዱ ግራኝም በኋላቸው እየተከታተለ በየካቲት ፳፪ ቀን በዓባይ ወንዝ ላይ እንደተገናኙ (እንደተዋጉ) ፤ በዚህም ቀን በሆነው ጦርነት አቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስና ልጃቸው ብእሴ እግዚአብሔር ቀኝ ጌታ ወሰንጉና ሌሎቹም ብዙዎቹ እንደሞቱ ቍጥር የሌለው ብዙ ገንዘብና ሰውም እንደተማረከ ይገልጽልናል ።

ግራኝ አህመድ እምና በ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. በክረምት የላሊበላን ቤተ ክርስቲያን አቃጥሎ በዚህ በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ያን ጊዜ አንጐት በሚል ሥያሜ ተጠቅሎ ይጠራ በነበረው በመቄት በኮረምና በሰቆጣ በኩል አልፎ በምን አኳኋን የትግሬን ታላላቅ አውራጃዎች እንደርታን ፤ አጋሜን ፤ ተምቤንን እንደበዘበዘ ከዚያ አልፎ አክሱም ደርሶ ከአክሱም በሺሬ ፤ በዋልድባና በአርማጭሆ በኩል አልፎ የሃይማኖት ወገኑ ከሆነው ከመዘጋው ባላባት ከመከትር ዘንድ አርፎ ያለፈውን ድካሙንና ጣመኑን ከተወጣ በኋላ አሁን ያገሬውን ሕዝብና በተለይ ሐሰን የሚባለውን የመከተርን የእህት ልጅ መሪ አድርጎ ጉዞውን ወደ ደንቢያ ዠመረ ።

ዋናው ዓላማው ንጉሡን አሳዶ ለመማረክ ነው ንጉሡም ከብዙ ቀን በፊት ቀድመው ሄደዋልና አትደርስባቸውም ቢባልም አድካሚውን ረጅም ጉዞ ያለ ዕረፍት ሌትና ቀን ለመድረስ ቆርጦ ተነሣ ። በእንዴት ያለ ብርታት ገሥግሶ እንደደረሰባቸው ሳይታወቅም አድብቶ ለመያዝ በምን አኳኋን ጭለማ ለብሶ እንዳዛቸው መከ

(1) «ወመርሕዎ እስከ ደምቢያ ንጉሥኒ ገብረ እንተ ደራ ወመለሳይኒ (ግራኝ) ተለዎ ድኅሬሁ ፤ ወተራከቡ በፈለገ ዓባዊ አመ ፳ወ፪ቱ ለየካቲት ፤ ወሞቱ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ወወልዱ ብእሴ እግዚአብሔር ወካልአን ብዙኃን ። ወጠፍአ ንዋይ ዘዓልቦ ኍልቈ ወቦ ዘተጼወዉ . . . . .» ታሪከ ነገሥት ገጽ 92 ።

ከል እንደገባ ፤ እንዳይታወቅም ራሱም የክርስቲያኖቹን ቋንቋ (አማርኛ) እየተናገረ ለሰዎቹም እንዲናገሩ አዞ እንደነበረ ይኸም ሁሉ ሆኖ ከደረሰባቸው በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በተአምራት ለጥቂት በፈረስ እንደምን እንዳመለጡ ይኸው በጦርነቱ ሰዓት አብሮት ያለው ዓረብ ፋቂህ ስለሆነ ከዚሀ እንደሚከተለው የሚለውን በእርሱው አነጋገር የአማርኛውን ትርጉም እናንብብ ።

«የሐበሻ ንጉሥ ይማም መዘጋ መድረሱን አያውቅም ነበር ። ነገር ግን አንድ መነኩሴ ወደርሱ ሄዶ በድንኳኑ ፊት ተደፋ (እጅ ነሣ) ። ንጉሡም ምን ወሬ አለ ? ብሎ ቢጠይቀው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ እስላሞች ደርሰውብሃልና እምልጥ ብሎ መለሰለት ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ መነኵሴው የሚለው እውነት መሆኑን እስቲ ሄዳችሁ መርምሩ ብሎ ፈረሰኞች ላከ ። እነሱም ወደሺሬ ወደሚወስደው መንገድ በግልቢያ ሄደው እየርን የሞላ ትልቅ አቧራ የቆመ አዩና ተመልሰው ለንጉሡ ነገሩት ። ይኸንንም ንጉሡ በሰማ ጊዜ በፍርሃት ከአለበት ቦታ (ከመዘጋ) ተነሥቶ የጐጃምን መንገድ ይዞ ሄደ ። ንጉሡ ወደጐጃም ለመሄድ በተነሣ በማግሥቱ ይማም ወደ መዘጋ መጥቶ ሠፈረ በዚያም ሳለ የሱልጣን መከትርን ልጅ አገባ ። በመዘጋም አሥር ቀን እንደተቀመጠ አሁን ተነሥቼ ንጉሡ አለበት ድረስ እየተከታተልሁ ላባርር ብሎ ፳ ፈረሰኛ የያዘውን ሐሰን የሚባለውን የሱልጣን መከትርን የእህት ልጅ ይዞ ተነሣ ። ሐሰንም ለ[illegible]ም መንገዱን እየመራው ወደ ተከዜ በሚወስደው መንገድ ሄደው በመዘጋ ውስጥ በሚገኝ ባንድ ተራራ ግርጌ ሠፈሩ ። ይማም ከርሱ ዘንድ በሄደ በ፫ኛው ቀን ሱልጣን መከትር ሞተ . . . . . . ። እህቱ ጋዮዋህ መሞቱን ለወታደሮቹ ደብቃ ወደ ይማም አህመድ ነገሩን ለመግለጽ መላክተኛ ላከች ።

ይማም በታከዚ (ተከዜ ?) ተራራ ሥር እንደሰፈረ የሱልጣን መከትርን ሞት ከመልክተኛው ስለሰማ ነጋሪት ያስመታ ዠመር፤እስላሞቹም ሁሉ በዙሪያው ተሰበሰቡ ። ለተሰበሰቡትም የሱልጣን መከትርን ሞት ገልጾ ናፊ የሚባለው ልጅ ባባቱ እግር መንገሡን ገለጸላቸው ። ናፊ ገና ወጣት ልጅ ስለነበረ ታስተዳድር የነበረችው የንጉሡ የመከትር እህት ነበረች ። እርሷም ምክር አዋቂና ብልህ ጥበበኛ የነበረች ሴት ነች ። ይማም የንጉሡን የእህት ልጅ ሐሰንን ወደ መዘጋ ተመለስና ለመከትር ልጆች እንዳባት ሁናቸው ብሎ ወደ አገሩ መለሰውና እርሱ ግን ጉዞውን ወደ ፊት (ንጉሡን ለማባረር) ገሥግሦ ደምቢያ እሚባል አገር ገባ ። ይኸም አገር በማናቸውም ረገድ ሀብታም የሆነ አገር ነው ። ዘወትር ሳያቋርጡ የሚፈሱ ወንዞች ፤ የለመለሙ አትክልቶች ሁሉ አሉት አገሩ ድርቀት አያውቅም ። መሬቱም አየሩም የሚስማማ በተራራና በጫካ ያልተሸፈነ ሜዳማ የሆነ መልካም አገር ነው ። የዚህን (ደምቢያን) አገር ፍሬና እህል የመሰለ በሌላው በአበሻ አውራጃ አይገኝም ።

ይማም በዚህ አገር ሆኖ ስለንጉሡ ወሬ መጠየቅ ዠመረ ። የአገሩም ሕዝብ እንደዚህ ሲል መለሰለት "ከኛ ዘንድ ከሄደ ፰ ቀን አልፎታል ፤ እርሱን ለመያዝ ብትከታተል ከሁለት ወር በኋላ ዳሞት ላይ ካልሆነ በቀር ልትደርስበት አትችልም" የዚህንም ጉዳይ በሚነጋገርበት ጊዜ አንድ ሰው ወደ አብድ ኢን ናስርና ወደሴዲ መሐመድ መጣና እዚህ አጠገባችን የንጉሡ ሀብት ይገኛል ብሎ ነገራቸው ፤ አብድ ኢን

ናስርም ወደ ይማም ሄዶ ቢነግረው ጦርህን ይዘህ ቅደምና ሂድ እኔም ነገ ወይም ተነገ ወዲያ እደርስብሃለሁ ብሎ አብድ ኢን ናስርን አዘዘውና ሌሊቱን የችቦ መብራት ይዘው ጉዟቸውን ቀጠሉ ። በዚሁም ሌሊት ይማም አብድ ኢን ናስርን ተከተለው ። እንደዚህም ሆነው ሲጓዙ የአብድ ኢን ናስር ጦር ደጀን የሆነውን የክርስቲያኖቹን ጦር ደረሰበት ከኋላ ደጀን ሆነው የሚጠባበቁትንም የንጉሡን ፈረሰኞች እስላሞቹ በተመለከቷቸው ጊዜ ይኸንኑ ለማስታወቅ ወደ ይማም መላክተኞች ላኩ ። መላክተኞቹም ይማም ከነጦሩ በጉዞ ደክሞ ለመሥፈር በሚያስብበት ሰዓት ደረሱና ነገሩት ። ከዚያ መሥፈሩን ትቶ ወደፊት ገሠገሠና ማታውኑ እንፍራዝ ውስጥ ደርሶ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አደረ (1) ። በማግሥቱም ተነሥቶ አብድ ኢን ናስር ቀድሞ በሄደበት መንገድ ጉዞውን ቀጠለ ንጉሡም ወዳለበት ለመድረስ ያራት ቀን መንገድ ቀረው ። የጭንትና የኮርቻው ከብት እስኪደክም ድረስ ሊትና ቀን ተጓዘ ።

በዚህ ጊት የእስላም ፈረሰኞች ወሬ ለመጠየቅ በያለበት ጋለቡ ፤ ከነርሱም ውስጥ አሊ ጎይታ ነበር ። እርሱም አቡን የሚባለውን የክርስቲያኖች ፈረሰኛ አግኝቶ ማረከው ። ይኸም አቡን የወዚር ሙጋሂድ (ሞጃሂድ) ወንድምና እስላም የነበረ በኋላ ሃይማኖቱን ክዶ ወደ ክርስቲያኖች የገባ ነው ። እርሱንም አሊ ጎይታ ይዞ ወደ ይማም አቀረበውና ወዴት ነበርህ ብሎ ቢጠይቀው ከንጉሡ ጋር ነበርሁ ፤ አሁን ግን ወደናንተ መጥቼ ለመደባለቅ ትናንትና ከንጉሡ ተለየሁ ብሎ መለሰ ። ይማም አሁን ብንከታተለው እንደርስበትምን ቢለው ብዙ አገር አቋርጦ ስለሄደ አትደርሱበትም ብሎ መለሰ ። በዚህ ጊዜ ይማም ይኸንኑ አቡንን አንድ ጊዜ መታና ምሕረት አድርጎ ለቀቀው ። የዚህም የአቡን ንግግር ከፍርሃት የተነሣ ውሸት ነበር ።

ISIC

ከዚያ እስላሞቹ አንድ ሰዓት ያህል እንደተጓዙ የንጉሡ መኝታና ወጥ ቤት የነበረውን ክርስቲያኖቹ ትተውት የሄዱትን አገኙ ። መብልም ገና ያላለቀ ነበረበት ። እስላሞቹ በዚህ ሥፍራ አንድ ሰዓት አርፈው ቁርሳቸውን ከበሉ በኋላ በእኩሉ ቀን ወደፊት በግሥጋሤ ሄደው ክርስቲያኖቹ ትተውት የሄዱትን ብዙ ድንኳን አዩ ። ሳጥንም ነበረበት ፤ እስላሞቹ ግን ስለዚህ ምንም ሳያስቡ ግሥጋሤያቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። ከሁሉም ፊት ቀድሞ የሚጓዘው አብድ ኢን ናስር ነበርና እስከ ተሲያት ድረስ እንደተጓዘ ወሬ ለመጠየቅ ፈረሰኞች አስቀድሞ ወደፊት ላከ ። እነሱም በንጉሡ የደጀን ጦር ደርሰው አይተው ተመልሰው ነገሩት እርሱም የሰማውን ወደ ይማም ላከ ፤ ይማም ግን ፈጽሞ ድካም መብዛቱን አይቶ ማረፍ ፈልጎ ነበር። ከመድከማቸውም የተነሣ የይማም ጓደኞች ሁሉ ወደኋላ ቀርተው ነበር ። ይማም የንጉሡን የደጀን ጦር እናንተ ባይናችሁ ዓይታችኋልን ብሎ መላክተኞቹን ጠየቀ።

(1) ከጐንደር ወደ እንፍራዝ ሲመጡ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ላይ ወደግራ ገባ ብሎ የሚገኘው ባኔ ዳዊት ዘመን የተተከለው ሰንደባ ኢየሱስ ነው ። ግራኝ በዚሁ አጠገብ መስፈሩን የቤተ ክርስቲያን አበው ይናገራሉ ።

መላከተኞቹም እኛ እራሳችን ባይናችን አላየንም ነገር ግን የኛ ጓደኞች ሄደው የን ጉሡን ደጀን ዓይተው ተመልሰው ነገሩን ብለው ነገሩት ። ይኸንን ንግግር እበቅሎው ላይ እንዳለ ከሰማ በኋላ ዠምበር እስኪጠልቅ ድረስ ተጓዘ ፤ ጐማራ (ከጐራ የሚመነጭ ወንዝ) እሚባለው ወንዝ ላይ ሲደርስ እስላሞቹ ሁሉ ከየበቅሏቸው ላይ እየወረዱ የጦር ልብሳቸውን እየለበሱ እፈረሳቸው ላይ እየወጡ ጉዟቸውን ቀጠሉ ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ በንጉሡ አጠገብ ወዳሉት የደጀን ወታደሮች መድረስ ቻሉ ። ከንጉሡም ጋር አንዱ ታኪ ሁለተኛው አውራይ አህመድ ዲን የሚባሉ ወገኖቻቸውን (እስላሞቹን) የከዱ ፪ ሰዎች ነበሩ ። ከነርሱም የመጀመሪያው ታኪ ጥሩ ፈረስ ስጠኝና ሄጄ እስላሞቹን ልግጠማቸው ብሎ ንጉሡን ጠየቀው እርሱም እሺ ብሎ ከሚሳቡት ፈረሶች አንዱን ዘቢል (ዞብል ?) የሚባለውን ሰጠው ፣ ታኪም እፈረሱ ላይ ወጣና ወደ እስላሞቹ ጋለበ ፤ አጠገባቸውም በደረሰ ጊዜ ወደ እግዚአብሐር ተጸጽቼ ንሰሐ ገብቻለሁ (ማረኝ) ብሎ ተናገረ ጓደኛው አውራይ አህመድ ዲንም እንደዚሁ ስለአደረገ ይማም ለሁለቱም ምሕረት አደረገላቸው ።

ይማም አህመድ ጦር የሚጓዝበትን ትልቅ አቧራ እስኪያገኝ እስከ ማታ ድረስ ተጓዘ አቧራውንም ባየ ጊዜ ለወገኖቹ እክርስቲያኖቹ መካከል ስትገቡ በነሱ ቋንቋ ተናገሩ ። እንጉሡ አጠገብ እስክትደርሱ ድረስ ከነሱ መካከል ማንንም በሰይፍም በጦርም አትምቱ ይኸን ያደረጋችሁ እንደሆነ በእግዚአብሔር ፈቃድ በድንገት ትማርኩታላችሁ ፈረሶቻችሁንም አዘጋጁ ብሎ መከረና በዚህ ዓይነት ሌሊቱ ጭለማ እስኪሆን ድረስ ተጓዙ ።

በጨለመ ጊዜ እስላሞቹ እኋላ ካሉት ከክርስቲያኖቹ ሴቶች ጋር ተደባልቀው አንድ ሰዓት ተጓዙ ። ቀጥሎም ሳይታወቁ ከፈረሰኛውና ከእግረኛው የክርስቲያን ጦር ተደባለቁ ። አንዳንድ ጊዜም እስላሞቹ አንዳንዶቹን ክርስቲያኖች እየመቱ ሲገድሏቸው መቺዎቹ እስላሞች መሆናቸውን ያልተገነዘበ ክርስቲያን ወታደር የንጉሥ ያለህ ወይም በአለቃው የእገሌ ያለህ እያለ ይጮህ ነበር ። ይማም አህመድ በነሱው ቋንቋ ተው አትምቱ እያለ እየጮኸ ይቆጣ ነበር ። እንደዚህ ሆነው እስኪ ጨልምና ውድቅት እስኪዞር ድረስ ከተጓዙ በኋላ እስላሞቹ ንጉሡን ለመሻት ሲሉ ወደ ግንባር ቀደሙ ጦር አልፈው ሄዱ ። አንዱ ክርስቲያን በደከመ ጊዜ ቆም ብሎ መብራቱን አብርቶ ዳቦውን ይበላ ነበር ። ከጨለማነቱ የተነሣ እስላሞቹ ባጠገቡ ሲያልፉ አያውቃቸውም ነበር እስላሞቹም እንዳይታወቁ የሚነጋገሩት በክርስቲያኖቹ ቋንቋ ነበር ።

በዚህ መካከል የችቦ መብራት ተበራና ዙሪያው ብርሃን ሆነ ፤ ይኸም ብርሃን አስደንጋጭ ነበር ። በዚያን ጊዜ እስላሞቹ ሰይፋቸውን እየመዘዙ ብርሃን ወደበራበት ሥፍራ ቢገሠግሡ ለካ ንጉሡ ሳይሆን ከንጉሡ እህቶች አንዲቱ ያለችበት ሠፈር ኖሯል ። እስላሞቹም ሲጠጉ መብራቱ ጠፋ እስላሞቹም መለስ ብለው ጉዟቸውን ቀጥለው ሲነጋ ሲል ንጉሡ በዓባይ ወንዝ በላይ በኩል ባለው ጠባብ መንገድ አድርጎ ሄደ . . . . . . ከጠባብነቱ የተነሣ ክርስቲያኖቹ በመንገዱ ለመተላለፍ ተጨናንቀው ይረጋገጡ ነበር ። ይማም በነሱ መካከል ሆኖ እንዳይሠራበት ሥፍ

ራው ስለአልተመቸ መሣሪያውን በእጁ ላይ አድርጎ አብሯቸው ሲጓዝ ክርስቲያኖ ቹም በተቀመጡበት ፈረስ ያጫንቁት ነበር ። ከክርስቲያኖቹም አንዱ የወዴት ነህ ብሎ ሲጠይቀው እገሌ የሚባለው የጦር አለቃ ነኝ ንጉሡን ለመርዳት መጥቻለሁ እያለ ይመልስ ነበር ፤ የርሱም ሹማምንቶች ሲጠየቁ እንደዚሁ እያሉ መለሱ ። በዚ ያን ጊዜ እገሌ ለእርዳታ ይኸው መጥቶ ደርሶልናልና ፋና (የሞራውን ጧፍ) አብሩ ብሎ ጮኸና ብርሃን ሲሆን ይማም አንዳንድ ክርስቲያን ገና መነጋገር አልቻለም ነበር ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖቹ (አወቁትና) በንጉሡ አጠገብ ሆነው ለመዋጋት ወደኋላቸው ተመለሱ ። ንጉሡ ይማም ወደፊቱ መቅደሙን አልተረዳም ነበር ።

ስለዚህ ይማም ወደኋላው ተመለሰ አንዳንድ እስላሞች ስለደረሱበት ንጉሡ ወደኋላ ነው ያለው ብሎ ነገራቸው ። ከዚያም ጎሕ እስኪቀድ ድረስ እመንገድ ላይ ቆሞ ይጠብቅ ገመር በዚህም ጊዜ አብሳማ ኑር ወደፊት ሄጁ ወሬ ጠይቄ ልምጣ ብሎ አምስት ፈረሰኞች ብቻ ይዞ ሄዶ ዓባይን ተሻገረ ። በፊቱ ክርስቲያኖቹ ለሽ ሽት የፈረሳቸውን ልጓም ለቀው ይጋልቡ ነበር ። አብሳማ ኑርም እነሱን ሲያባርር አንዱን የክርስቲያን ፈረሰኛ ደርሶ ማረከው ። ይኸም የተማረከው አናስ የሚባለው እስላም የነበረና በቅዳ ላይ ከደገልሃን ልጅ (ከተክለ ሃይማኖት) ጋር ከድቶ ወደ ንጉሡ የመጣ ከዳተኛ እስላም ነው ። እርሱም የይማም አሽከር የነበረ ጊዜ በጥፋት ሁለት እጁን የተቆረጠ ነበር ። አናስም እንደተያዘ ያውልህ ያ እየጋለበ የሚሸሸው የሀበሻው ንጉሥ ነው ብሎ ለአብሳማ ኑር ነገረው ። አብሳማ ኑርም ንጉሡን ለመ ያዝ ሮጠ (ጋለበ) ። ነገር ግን ንጉሡ የተቀመጠበት ፈረስ ፈጣንና ከጥሩ ዘር የተወ ለደ በመሆኑ እንኳን ንጉሡ ሊያዝ አብረውት ከሚጋልቡት ከዓቃቤ ሰዓቱ (ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ) በቀር አንዱም አልተገኘም ። ዓቃቢ ሰዓት ማለት የክርስቲያ ኖቹ ቃዲ (መንፈሳዊ ሹም) ነው ። እርሱም ከፓትርያርኩ (ከጳጳሱ) ቀጥሎ ፪ኛ ማዕ ርግ አለው ። ክርስቲያኖቹ ሁለት የቤተ ክህነት አለቃ አላቸው አንዱን ከግብጽ ሺ ወቄት ወርቅ ከፍለው ያመጡታል እርሱንም አቡን ይሉታል ። ፪ኛውን ግን አበሻ ውን (እጨጌ) ከመካከላቸው ይመርጣሉ ። የሃይማኖታቸው መሪ እርሱ ነው ፤ ከመ ንግሥቱ ሩቡ የርሱ አበል ነው ። አብሳማ ኑር ዓቃቤ ሰዓቱን ይዞ ንጉሡ አለመሆ ኑን በተረዳ ጊዜ ወዲያው ገደለው . . . . . ዓመተ ድንግል የምትባለው የንጉሡም እህት ተማረከች ። ይማምም በጉጃም አንድ ወር ያህል ተቀመጠ ።» ሲል ግዕዙ ከኋላው ተከታትሎ ዓባይ ላይ ተገናኙ ፤ ዓቃቢ ሰዓት ነገደ ኢየሱስና ልጁ ብእሴ እግዚአብሔር ሞቱ ፤ ብዙ ገንዘብ ጠፋ ሰውም ተማረከ ብሎ አሳጥሮ ያለፈውን ዓረብ ፋቂህ በዚህ ዓይነት ዘርዝሮ ያቀርበዋል ። እርሱም ይኸን ሁሉ ጽፎ ሲጨርስ ለግራኝ ገጥሞለታል (1) ። ግጥሙን በትክክል በአማርኛ መተርጐም ችግር ነው ። ይልቁንም ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊ ከተተረጐመ በኋላ አሁን ደግሞ ከፈረንሳዊ ወደ አማርኛ ሲተረጐም የግጥሙ ወዝ ይጠፋል ። የነገሩን ስልት መጠበቁና ይልቁንም ቤት እያስተካከሉ መምታቱም ያስቸግራል ። አሳቡ ግን ይህ የሚቀጥለው ነው ።

ISIC

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 430 - 439

፩ - የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ስለዚህ ጦርነት እንደዚህ ብሎ ይገጥማል ።

፪ - የጦር አንበሳው የኢብራሂም ልጅ እግዚአብሔር የምትፈልገውን ሁሉ በሙሉ ሰጠህ ።

፫ - ከፈረሰኞችህ ጋር አገሩን ሁሉ አቋረጥህ ከሰዓድ ዲን (ከአዳል) አገር ዠምሮ እስከ ናቢላ (1) ያለውን አገር ሁሉ ያዝህ ።

፬ - ከዚያ ተመልሰህ ከነወታደርህ ጐጃም መካከል ሠፈርህ ።

፭ - አገሩን በረሃውን ደምቢያን እንፍራዝን ኤጋላን (ቁናማ ውስጥ) አቋርጠህ አለፍህ ።

፮ - ንጉሠ ነገሥቱ ከነወታደሩ ሲሸሽ አደረ እናንተም (ይማም ከነወታደሩ) ከጧት ዠምሮ አባረራችሁት ።

፯ - በጭለማ እንደ ፈጣን ጐርፍ ሌሊት ደርሳችሁ በጭለማ ተደባለቃችሁበት ።

፰ - የክርስቲያኖቹን አንገት እየቆረጣችሁ በዓባይ መካከል ቅጥ አጥቶ ጦሩ እንዲዘባረቅ አደረጋችሁት ።

፱ - እስላሞቹ ለመብልና ለእንቅልፍ ሳይጓጉ መሣሪያቸውን እንደያዙ በፈረስ ነበሩ ።

፲ - ሁለት ቀን አንድ ሌሊት ተጉዘው በ፫ኛው ሌሊት ምርኮ የነርሱ ሆነ ።

የዓረብ ጸሐ[illegible]ያገራችን ያማርኛም ሆነ የግዕዝ ጸሐፊ ሁሉም ከሴማውያን ዘር የወረዱ እንደመሆናቸው መጠን ያጻጻፋቸው መንገድ ይመሳሰላል ባገራችን ድርሳንም ገድልም ታሪክም ጽፈው ወደ መጨረሻው መልክዕ ወይም ግጥም አድርገው በመልክዑ ወይም በግጥሙ በአጭር ንግግር ሙሉውን የባለጉዳዩን ጠቅላላ ሥራ መጥቀስ ልማዳቸው ነው ።

ዓረብ ፋቂህም ይኸን ግጥም ለግራኝ አህመድ የጻፈበት ምክንያት በዚሁ ዓይነት የግራኝና የጦሩ የ፫ ቀን ግሥጋሤ አስደንቆት ነው ። ይሁን እንጂ ዓረብ ፋቂህ የዚህን የጦርነት ታሪክ እፍጻሜ አላደረሰም ። ገና ወደፊት ግራኝ ከጐጃም ወደ ትግሬ መመለሱን ከጦር ሹማምንቱ ውስጥ ወዚር አዶሌ ከተስፋ ልዑል (አቃጽን ሠራዊ) ጋር ሲዋጋ መሞቱን ፤ ተስፋ ልዑልም በተራው በወዚር አባስ እጅ መሞቱን ይተርከልናል ።

የሆነ ሆኖ በዚህ በዓባይ ዳር ግራኝ ንጉሡን ከነሕይወታቸው ለመማረክ ያደረገው ጥረት ንጉሡም አብሳማ ኑር ሊማርካቸው ሲል ለጥቂት ማምለጣቸው ለአንባቢ የሚያስደንቅ ነው ። ግራኝና ጦሩ በሌሊቱ ጨለማ ተጠቅመው ከንጉሡ ሠፈር ተደባልቀው ሊማርኳቸው ሲሉ እርሳቸውንም በመጨረሻ ከምርኮ ያዳናቸው ጥሩው ፈረሳቸውና ይኸው የሌሊቱ ጊዜ ጭምር ሳይሆን አይቀርም ። በዚህ ዓይነት ጭለማው ለሁለቱም ባላጋራዎች ጠቅሟል ፤ ሁለቱንም ጐድቷል ማለት ነው ። ሌሊቱን ግራኝ ከነሹማምንቱ እጦራቸውና እርሳቸው መካከል ተደባልቆ አንዳንድ ጊዜም ከክርስቲያኑ መካከል ቀስ እያለ እስከማስገደል ደርሶ የነርሱን ቋንቋ እየተነ

(1) ሙሴ ረኔ ባሴት በ440 ገጽ ቍጥር 2 ይኸን አገር ባቢላ ብለውታል ግብጽን ማለቱም እንደሆነ በነርሱም አነጋገር ግብፅ እንደ ባቢሎን ባጭሩ ባቢላ ይሉታል ብለዋል ።

ጋገረ አንድ ጊዜ ወደፊት አንድ ጊዜ ወደኋላ እየተመላለሰ ያሉበትን እየሰለለ እያ ደባ ከነሕይወታቸው ለመያዝ በጣም ከጣረ በኋላ ሳይሆንለት የቀረው ምናልባት በደህናው ጊዜ ዘውድ አድርገው ዣንጥላ ወይም ድባብ አሲዘው በግርማ ይሄዱ የነበሩትን ትተው በአሁኑ አስጊ ጊዜ ሰላይና ከዳተኛ በበረከተበት ሰዓት እንደማ ንም ሰው አልባሌ መስለው ስለሚጓዙ ይሆናል ። እስላሞቹ ከክርስቲያኖቹ ሠፈር በተደባለቁ ጊዜ የክርስቲያኖቹን ንግግር እንዲነጋገሩ ግራኝ አደራ ጭምር ማዘዙ ንና እስላሞቹም መነጋገራቸውን ስለሚገልጽ እስላሞቹና ግራኝ ራሱ እንደምን የክ ርስቲያኖቹን ቋንቋ ተነጋገሩ ቋንቋውስ ምን ዓይነት ነበር አማርኛ ይሆን ወይስ ግዕዝ የሚል ጥያቄ በአንባቢ ላይ ይመጣበታል ።

ስለመዠመሪያው ጥያቄ ። በክርስቲያኖቹ ውስጥ ካፄ ልብነ ድንግል ጋር ብዙ እስላሞች የአዳልና የሱማሌ ቋንቋ የሚናገሩ ፤ በግራኝ አህመድ ውስጥ ብዙ ክርስቲ ያኖች ኢትዮጵያውያን ግዕዝና አማርኛ የተደባለቀበትን የዘመኑን ቋንቋ የሚናገሩ ወታደሮችና ሹማምንቶች አሉ ። በምርኮ ስም ወይም ሹመት አነሰኝ የሚለው እየ ተቀየመ ፤ ቅጣት የደረሰበት ወይም እንዳይቀጣ የፈራው ሁልጊዜ ከዚያ ወደዚህ ፤ ከዚህ ወደዚያ እየሄደ ይኖራል ። ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ እንኳን "ጥሩ ፈረስ ይሰጠኝና እስላሞቹን ልውጋ" ብሎ አታሎ በተቀበለው ፈረስ ሮጦ ወደ እስላሞቹ የተደባለ ቀውን ታኪንና አውራይ አህመድን ፤ አናስን ማስታወስ ይበቃል ። ከዚህም ጋር በአዳልና በሱማሌ ወሰን ላይ የሚገኙት የደዋሮ ፤ የይፋት ፤ የፈጠጋር የባሌ ሕዝ ብና ሹማምንት ሁሉም ባይሆኑ አጋማሾቹ የሁለቱንም ወገን ቋንቋ መናገራቸው ባሁኑ ሰዓት ደግሞ ከግራኝ ጋር ያሉት የበለው ነገዶች አማርኛም ትግርኛም አገው ኛም እንደሚያውቁ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ግራኝ ቀድሞም በቤተ አምሐራ (ዋስል) አሁንም በዚህ በዓባይ ዳር አዘንግቶ ወይም አደጋ ጥሎ ለመማረክ እንዲመቸው ሲል በክርስቲያኖቹ ቋንቋ ተናገሩ ብሎ ያዘዘው እነዚህኑ መሆን አለበት ። እራሱም ያልተጣራ ትንሽ ትንሽ የክርስቲያኖቹን ቋንቋ ይናገር እንደነበረ ዓረብ ፋቂህ በትክክል ገልጾልናል ። ግራኝ አድብቶ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጦርና ጓዝ መካከል ሲጓዝ አንተ ከወዴት መሆ ንህ ነው ብሎ አንዱ የክርስቲያን ወታደር ቢጠይቀው እኔ ንጉሡን ለመርዳት የመ ጣሁ ነኝ ብሎ የመለሰለትን እንብበናል ። ይህ የክርስቲያኖቹ ቋንቋ ምን ዓይነት ነበር ፤ የዛሬው ግዕዛችን ወይስ አማርኛችን ይሆን ለተባለው መልሱ ከዚህ በታች እንደመጠኑ ይቀጥላል ።

መቸም የዚህን ዘመን ቋንቋ ከ፲፫ኛው መቶ ዠምሮ አማርኛ መሆኑ እርግጥ ነው ፤ ይሁን እንጂ ዓይነቱን በትክክል የሚያስረዳ በሰፊው በዚሁ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍም ሌላም ደብዳቤም ስለሌለ አፍ ሞልቶ ለመናገር ሁልጊዜ እንዳዳገተ ነው ። በዚህ ዘመን የተጻፈው መጽሐፍና ደብዳቤ ሁሉ እስከዘመናችን ደርሶ የምን መለከተው ሁሉ በግዕዝ ቋንቋ ነው ። የግዕዝ ቋንቋ ግን የቤተ ክህነት ፤ የሊቃው ንት ፤ የጽሕፈት ቋንቋ ነው እንጂ የሕዝብ ቋንቋ አልነበረም ። ነገር ግን አማርኛ የተባለው የሕዝቡ ቋንቋ ከግዕዝና ከአማርኛ የተደበላለቀ ሌላ ቋንቋ ነበረ ፤ ከግዕ

ዝና ከአማርኛም ተደበላልቆ በተገኘው ቋንቋ ላይ አንዳንድ የአዳልና የሱማሌ ምና ልባትም የአገው ቋንቋ ሳይጨመርበት አልቀረም ። ያዔ ልብነ ድንግል ስመ መንግሥት ወናግ ሰገድ ተብሎ በዚሁ ነዋሪ ሆኖ ሲጠሩበት ወናግ የተባለው ከግዕዝና ከአማርኛ የተለየ የአዳሎች ቋንቋ መሆኑ ትርጓሜውም አንበሳ ማለት መሆኑ ብዙ ጊዜ ተነግሮአል ። አንበሳ ሰገድ በመባል ፈንታ ወናግ ሰገድ ሲባሉ የአዳል ቋንቋ በግዕዙና በአማርኛው መካከል እንደተቀየጠና ይኸም ልማድ ሆኖ እንደሚሠራበት ያስረዳል ። እንደዚሁም ለሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በጻፉት ደብዳቤ ላይ ስነግሥ ዳዊት ተባልሁ ። ጥምቀትን የተቀበልሁለት ግን ዕጣነ ድንግል ተባልሁ ሲሉ ልብነ ድንግል በማለት ፈንታ ዕጣነ ድንግል ማለታቸው የአማርኛ ቋንቋ በዘመናቸው ይሠራበት እንደነበረ ያስረዳል ።

የሆነ ሆኖ የዘመኑ ያማርኛ ቋንቋ ከግዕዝና ከአማርኛ የተውጣጣ ቋንቋ ምን ዓይነት መሆኑን ወደፊት ባዔ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ላይ በሰፊው እስከና መለከት ድረስ አሁንም ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ በሰበሰቡት ታሪክ ነገሥት ላይ የሚገኘው ስለራሱ ስለግራኝ የተገጠመው የመቃወም እንጂ የምሥጋና ያልሆነው ግጥም በመጠኑ ያሳየናል ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ።

፩ - ግራኝ በኢትዮጵያ ነግሦ ነበር
፪ - ንዋየ ቅድሳት ሲመዛዝር (ሲመዘብር ?)
፫ - በማመድ ሲያዘምር.....
፬ - ማዕተብ ካንገት ሲመትር
፭ - ታቦት ኢያሰበር
፮ - ቢያነግሥሕ እግዚአብሔር
፯ - በዳዊት መንበር
፰ - ቍጥዓ እንደ ጸጅ ሰከር
፱ - ሰላጢን እንደዘንግ ወረወር.....
፲ - ለገዳይ ተኩር.....
፲፩ - እንደ አንበሳ ሲጥህር.....(1)

ይህ በግራኝ ላይ በዘመኑ ወይም ዘመኑ ባለፈበት በዚያው ሃምሳ ዓመት ውስጥ የተገጠመው ግጥም የዘመኑን ቋንቋ ለማስረዳት ያህል ይበቃል ።

በዚህ ዓይነት ከይኵኖ አምላክ ዠምሮ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ ቀጥሎም በጐንደር መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ ይኸን የመሰለው ቋንቋ እየተሻሻለ እስካሁን አለው አማርኛችን ላይ ደረሰ ። ቋንቋ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሻሻለ መለወጡ በኛም በሌላውም አገር የታወቀ ነው ፤ በቅርቡ ባዔ ቴዎድሮስ ዘመን ወይም ባዔ ዮሐንስ ዘመን የሚነገረውና የሚጻፈው አማርኛ በዛሬው ዘመን ከሚጻፈው ጋር በመሠረት ሳይሆን በአነጋገር ቅርጽና በአረፍተ ነገር አሰካክ ይለያያል ።

የሆነ ሆኖ ይህ በዚያ ዘመን ቋንቋ ስለግራኝ የተገጠመውን እንደተቻለኝ ወደ

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 91

ዛሬው አግርኛ ወስጇ ለማብራራት ከዚህ እንደሚከተለው እሞክራለሁና ቍጥሩን ከቍጥሩ ጋር እያገናዘቡ መመልከት ነው ። በፊተኛው ላይ ቍጥር አልነበረም ለማ ስተያየት የጨመርሁበት ራሴ ነኝ ።

፩ - ግራኝ በኢትዮጵያ ነግሦ ነበር (ግልጽ ነው)
፪ - የቤተ ክርስቲያንና የገዳም የተቀደሰ ሀብት ሲበዘብዝ ወይም ሲዘርፍ
፫ - ለነቢዩ ለመሐመድ መዝሙር (ከቁራን) እያስዘመረ
፬ - ከክርስቲያን አንገት ላይ ማተብን እያስበጠሰ
፭ - ታቦት እያሰበረ (ግልጽ ነው)
፮ - እግዚአብሔር በዳዊት መንበር (በሰሎሞን ተከታዮች ዙፋን) ቢያስቀምጥህ
፯ - ፰ - አንተ ግን ቁጣህና ግፍህ እንደ ጠጅ የሰከረ ሆነ (ወይም ቁጣህ እንደ ጠጅ ፈላ)

፱ - ሰለጢን እንደ ዘንግ ወረወር ሲል ሰለጢን የሚለው ሱልጣን ሊሆን ይችላል ወይም ሰላህ - ዲን አቡበከር የሚባለውን የሐረርን ሱልጣን ገድሎ ሥልጣ ኑን ስለቀማው ይሆናል ።
፲ - ለተኩስ ወይም ለአገዳደል (ዓይንህ አተኳሪ) አነጣጣሪ
፲፩ - እንደ አንበሳ ሲጮህ (በውጊያ ጊዜ የሚያደርገውን ፉከራ ይሆናል)

ISIC

## ምዕራፍ ፹፭

## የዓቃቤ ሰዓትና የእጨጌ ልዩነት - ስለ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስና ስለቀኝ ጌታ ወሰንጌ ሞት

ዓረብ ፋቂህ በዚህ በአለፈው ምዕራፍ የግራኝ ጦር ያለ ዕረፍት በመገሥገሥ ባዔ ልብነ ድንግል ሠፈር ደርሶ ሳይታወቅ በሌሊት ጉዞ ተደባልቆ አብሮ እየተጓዘ፣ አንድ አንድ ጊዜም ሲመቸው ክርስቲያኑን እየገደለ ፤ ሟቹም የመታው ጠላት መሆኑን ሳያውቅ የንጉሥ ያለህ እያለ እስኪጮህ የጠላቱ መሪ ግራኝ የወገን ሹም መስሎ "ተው አትምታው" እያለ እስኪያታልል ድረስ በግራኝ የአመራረክ ዘዴ ዋናው ጦር ባንድነት ታጅቦ በመድረስ ፊንታ ከፊትና ከኋላ ተበታትኖ የክርስቲያኑ ጦር ሳያውቅ ከሠፈር ገብቶ ተደባልቆ የሚጓዘው በነ አብሳማ ኑር በነአብድ ኢን ናስር መሪነት ቀድሞ የደረሰው ነው ማለት ነው ። የፕላኑ ዋና ዓላማ በዚህ ዓይነት ተደባ ልቆ በድንገት ንጉሡን አዘንግቶ ለመማረክ ነበር ።

ንጉሠ ነገሥቱና ምናልባት ብዙ ቤተሰብም ከምርኮ ሊያመልጥ የቻለው በክር ስቲያኖቹም በኩል እንደዚሁ ጥርጣሬ ገብቶ በመጠኑ ተለያይተው ስለሚጓዙ ይሆ ናል ። በዚህ ላይ ደግሞ ከእያቸው በኋላ ሲያባርራቸውና እርሳቸው ዘሩ ጥሩ በሆነ ፈጣን ፈረስ ጋልበው ሲያመልጡ ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌልና ልጆቹ እንደ ምን ሆነው እንዳመለጡ ወይም በጉዞው ውስጥ ይኑሩ አይኑሩ አይታወቅም ። ከንጉ

ሣዊ ቤተሰብ ውስጥ ከንጉሡ እኅት ከዓመተ ድንግል በቀር የተማረከ መኖሩን ዓረብ ፋቂህ አልጻፈም ። ምናልባት ያ መነኩሴ የእስላሞቹን መጠጋት ከሠፈር መጥቶ ላዒ ልብነ ድንግል ከነገረበት ቀን አንሥቶ እቴጌይቱ ፈረስ ለመጋለብ የማይችሉትን ሕፃናትና ሴቶች ይዘው በቅድሚያ ሌትና ቀን ሄደው አባይን ተሻግ ረው ጐጃም ወደ ዘመዶቻቸው አገር ሄደው ተቀምጠው ይሆን ወይም ወደ ተራራ ማው አገር ወደ ሰሜን ቀርተው ይሆን አይታወቅም ።

በተረፈ ዓረብ ፋቂህ የመጠሪያ ስሙን ሳይጠቅስ የዐቃቤ ሰዓቱን በአብሳማ ኑር መገደል የዐቃቤ ሰዓቱም ማዕርግ ከጳጳሱ ቀጥሎ ፪ኛ መሆኑን በወሬ እየጠየቀ የጻፈውን እንብበናል ። በስሕተትም የእጨጌውን ሥፍራና የሲሶውን አበል ለርሱ መድቦታል ። ነገር ግን የእጨጌውና የዐቃቤ ሰዓቱ ማዕርግ አበላቸውና ሹመታ ቸው ሥልጣናቸውም በፍጹም የተለየ ነው ። ከመሠረቱ እጨጌው በደብረ ሊባኖስ በመንበረ ተክለ ሃይማኖት የሚቀመጥ ሲሆን ዐቃቤ ሰዓቱ በሐይቅ ፤ በደብረ እስጢ ፋኖስ መንበር የሚቀመጥ ነው ። ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ አዘጋጀው የሚባለው ታሪከ ነገሥት የሁለቱን የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች መብትና ተግባር ለይቶ ሲያ መለክት እንደዚህ ብሏል ። «በአቡነ ጌ(ቄ)ርሎስ ፤ በሐይቅ መምህር ፤ በአባ ኢየሱስ ሞዓ ፤ በደብረ ሊባኖስ መምህር ፤ በክቡርና የአባቶች እናት በሆኑት በብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎትና እርዳታ መንግሥትን ከዛጕዬዎቹ ስለአስመለሱ ለዚሁ ውለታ ከመንግሥቱ እጅ አንዱን እጅ የእጨጌነት ማዕርግ ጨምሮ ለተክለ ሃይማ ኖት ፤ ለአባ ኢየሱስ ሞዓና ለተከታዮቻቸው የዓቃቤ ሰዓትነት ማዕርግ በመሐላ ሰጣቸው . . . . . . .» (1) ። በአጻጻፉ ከጳጳሱ ቀጥሎ አባ ኢየሱስ ሞዓን ስለአስከ ተለ ዓረብ ፋቂህ የሰማውና የጻፈው እውነት ይሆን ? ባዒ ልብነ ድንግል ዘመን ከእ ጨጌው በአበልና በአስተዳደር ሳይሆን በወግና በማዕርግ ዓቃቤ ሰዓቱ ይበልጥ ይሆን የሚል ጥርጣሬ ሊያድር ይችላል ።

አባ ኢየሱስ ሞዓ መደባቸው በ፲፰፻፳፭ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲ ቀን የተበዘበዘው የሐይቁ የቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም መምህር (አበምኔት) ሲሆኑ ተክለ ሃይማኖት ያሉ አቡበክር ቀጢን ትእዛዝ አውራይ አቡበክር (የበለው ነገድ) በ፲፰፻፳፫ ዓ. ም. ያቃጠለው የደብረ ሊባኖስ መምህር ሲሆኑ ይኸን አበልና የማዕርግ ስም በመሐላ ለሁለቱ አባቶች የሰጠው ይኩኖ አምላክ መንግሥትን ከማግኘቱ በፊት እየተማረ ያደገው በሐይቅ አባ ኢየሱስ ሞዓ ዘንድ መሆኑን ከዚህ በፊት በሰፊው አመልክተ ናል ። በዕድሜም በአባትነትም ከተክለ ሃይማኖት ኢየሱስ ሞዓ ስለሚበልጡ ምና

(1) ለይኩኖ አምላክ ዘሚጠ መንግሥተ እምነ ዛጔ ብጸሎተ ጳጳስ አባ ጌርሎስ ፤ ወበጸሎተ አባ ኢየሱስ ሞዓ መምሕረ ሐይቅ ፤ ወበትንብልናሁ ለአብ ብፁዓዊ ክቡር ርዕሰ አበው አቡነ ተክለ ሃይማኖት መምህር ዘደብረ ሊባኖስ ፤ እስመ ነበሩ በመዋዕሊሁ ኮሉ ኖኅ መንግሥቱ ወበእንተዝ ወሀቦሙ ለውሉዱ ፩ እደ እም ፪ እድ መንግሥተ ወምኵናነ ወሥልጣነ ውሂመ እም ውሉደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እጨጌ በኪዳን ወመሐላ ፤ ወእምውሉደ አባ ኢየሱስ ሞዓ ዓቃቤ ሰዓት ከመ ይኩን ሎሙ ርስተ ለትውልደ ትውልድ ። የኢት. ታሪክ ካዔ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 11 ገጽ 13 - 14 ፤

ልባት ከወደ መገመሪያው ጊዜ ላይ (፲፪፻፷ - ፲፩፻ ዓ. ም.) ኢየሱስ ሞዓ ወይም ተከታዮቻቸው ከተከለ ሃይማኖትና ከተከታዮቻቸው በማዕርግ የበለጡበት ጊዜ ይኖራልና የዓረቡን አጻጻፍ በሙሉ ማስተሐቀር አይቻልም ። ነገር ግን ካዔ ዘርዓ ያዕቆብ ይሁን ወይም ካዔ ልብነ ድንግል ወዲህ ይልቁንም በጐንደር መንግሥት የእጨጌው ሥልጣንና ክብር ከዓቃቤ ሰዓቱ እየበለጠ ሄዷል ። በጥንታዊው ሥሬትና ደንብ ብዙ በየጊዜው የተለዋወጠ ነገር አለ ። የእጨጌው እንዳለ ክብሩም ሥልጣኑም ሳይነካ በከፍተኛ ደረጃ ኑሮውን ሲቀጥል የዓቃቤ ሰዓቱ እየተፋለሰ ነገሥታቱ በተለይም በጐንደር መንግሥት ዘመን እንደልባቸው ሥልጣኑን ከፍም ዝቅም እያደረጉ ዘርም ሳይለዩ ሲሾሙ ሲሽሩበት መኖራቸውን አሁንም ይኸው ታሪከ ነገሥት ወደ መጨረሻ ላይ እንደዚህ ሲል ያወሳዋል ። «ይህ ሥርዓት ሳይፈርስና ሳይናወጥ እስከ ዛሬ የቆየውን ከርሱ በኋላ የነገሡት ይኵኖ አምላክ በሕያው እግዚአብሔር በመሐላ ያጸናውን የዓቃቤ ሰዓቱን ኪዳን አፈረሱት» (1) ።

ጽሑፉ እስከ ማን ዘመነ መንግሥት ድረስ ጸንቶ በማን ዘመነ መንግሥት የዓቃቤ ሰዓቱ ወግና ሥሪት ተሽሮ እንደተሾመበት ዘመንና ስም ለይቶ አይገልጽም ። ቢሆንም በዚህ ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን የዓቃቤ ሰዓቱን ክብር ስናመዛዝን ታሪከ ነገሥቱ «የዓቃቤ ሰዓቱን ወግ በኋላ የተነሡ ነገሥታት አፈረሱት» ያለው ከልብነ ድንግል ወዲህ በጐንደር ዘመነ መንግሥት የነገሡትን ማለቱ ይመስላል ።

ISIC

የሆነ ሆኖ የመንግሥት ሥልጣን ከይኵኖ አምላክ እስከ ዓዔ ልብነ ድንግል ድረስ (፲፪፻፷፰ - ፲፭፻፴፪) በነገሡት ነገሥታት እጅ በነበረበት ሰዓት በተለይ በአሁኑ ባዔ ልብነ ድንግል ጊዜ ሁኔታው ሲታይ ዓቃቤ ሰዓቱ የመንፈሳዊና የሥጋዊ ሥራ ድርቦ የያዘ ፤ የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ባለሥልጣንና አማካሪ ሆኖ ይታያል ። ኑሮው የርሱ በቤተ መንግሥቱ ሲሆን የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ በብርቅ ካልሆነ በቀር ተቀማጭነቱ በዚያው በገዳሙ በደብረ ሊባኖስ ነው ። እጨጌ ፊልጶስ ዓምደ ጽዮንን ለመገሠጽ እንደመጣ እነዚህም ለምክርና ለተግሣጽ ካልሆነ በቀር የደብረ ሊባኖስን መንበራቸውን ትተው ወደ ቤተ መንግሥቱ መጥተው የሚቀመጡ ፤ የአስተዳደርም ሥልጣን የያዙ አይመስሉም ።

ዓቃቤ ሰዓቱ ግን በቤተ መንግሥቱ ተቀማጭ የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ባለሥልጣን ደረጃው ከራስም ከቢትወደድም በላይ ከንጉሡ ቀጥሎ መሆኑን ሥርዓተ መንግሥትና ታሪከ ነገሥት የሚባሉት አሥረጅ ጽሑፎቻችን የቤተ መንግሥት ወግና ሥርዓት ሲጽፉ በምክር ጊዜ ከእገሌ ቀጥሎ እገሌ ይመክራል ሲል ከታች ከአዳል ጭፍራ ይገመርና የቀሩትን ሹማምንት እያዳረሰ መጥቶ ጸሐፌ ላምን ፤ ጐጃም ነጋሽን ፤ ቤጌምድር አዝማችን ፤ ስሜን አጋፋሪን ፤ ትግሬ መኰንን ታላቅ ብላቴን ጌታን ቢትወደድን (ራስ ቢቶደድ) እያከታተለ ይጠቅስና ከዚያ ዓቃቤ ሰዓት ከዓቃቤ ሰዓቱ በኋላ በመጨረሻ ንጉሡ በሚወስነው ፍጻሜ ይሆናል ስለሚል

(1) "ወዝኒ ሥርዓት ሐለወ ወኢፈለሰ እስከ ይእዜ ። ለዓቃቤ ሰዓትሰ አፍለስዎ ካልዕ ነገሥት ዘእምድኅሬሁ ሥዒርሙ ኪዳነ ዘመሐለ ሎሙ ይኵኖ አምላክ በስመ እግዚአብሔር ሕያው ።" ታሪከ ነገሥት ፓሪስ ቤ. መ. በቍጥር 143 የተቀመጠው ገጽ 32 ፤

የዓቃቤ ሰዓቱ ደረጃ በአስተዳደር በፍርድ በምክር ከቢትወደዶቹና ከራሶቹ ... ከንጉሡ በታች መሆኑን ያሳያል ። የራስና የቢትወደድ ደረጃ በዚህ ጊዜ እንደ... በትክክል የተለየ አይመስልም ። ባንድ ቦታ ላይ የግራ ወይም የቀኝ ቢትወደድ ... ውን ያንኑ ሰው በሌላ ቦታ ራስ ይለዋል ። ይህ የዓቃቤ ሰዓት ከፍተኛ ደረጃ ... ልብነ ድንግል ዘመን በዚህ ዓይነት ሲታይ «ሌሎች ነገሥታት አፈረሱት» እ... ለው በጐንደር ዘመነ መንግሥት የዓቃቤ ሰዓቱ ደረጃ ወደታች ... ከአክሱም ንቡረዕድ በላይ ከታላቅ ብላቴን ጌታ በታች መሆኑን ... መዋዕል ያመለክታል (ጉይዲ ያሳተመው ኮርፑስኮ ያደሰው ገጽ ፪፻ ፶፫) ... ረሻ ደግሞ እያደር ተዳክሞ ከሁሉም ዝቅ እያለ መጥቶ እስከመጥፋት ደርሷል ።

ስለዚህ አሁን አብሳግኑር ንጉሡን ያገኘ መስሎት በፈረስ አባር ... አለመሆኑን ካወቀ በኋላ የገደለው ዓቃቤ ሰዓቱ የመጠሪያ ስሙ ነገደ ኢየሱስ ... ኑን የሚያስረዳን ዓጼ ልብነ ድንግል ለአክሱም ጽዮን ፣ ለእምባ ሠነይት ... ሮቢል ጉልት እየጐለቱ እሰጡበት ጽሑፍ ላይ ብዙ ጊዜ የርሱን ስም ከ... እየቀጠሉ ጽፈውታል (1) ። አንዳንድ ጊዜ ከራሳቸው የባለቤታቸውን ... ሳን (ሰብለ ወንጌል) እንደዚሁም ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ የገቡ እንደሆን ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ፫ኛ ደረጃን ይይዛል (2) ።

ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ፖርቱጋሎቹ ከአሥር ዓመት በፊት ... እየተቀበለ ያነጋገራቸው ፣ ከብዙ ቀን ደጅ ጥናት በኋላም ወደ ንጉሡ ... ኞቸው እርሱ ነው ። ብዙ ጊዜ ከዚህ በፊት ስሙን ደጋግመን ያነሣነው ... አልቫሬዝ ወዳገሩ ገብቶ በ፲፭፻፵ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፉ ላይ ... ዓቃቤ ሰዓት እንደዚህ ይላል «ትልቅ የሐር ቆብ የሚያ የንጉሡ ነገሥቱ ... ዘመድ ነው የሚሉት አንድ ሽማግሌ ወደኛ መጣ ። ይህ ሰው ዓቃቤ ሰዓት ... ስኝ የማዕርግ ስም የሚጠራ በአገሩ ውስጥ ያለ ሁለተኛ ታላቅ ሰው ነው» ...

በዚህ ዓይነት ከብዙ ዘመናት ምናልባት አልቫሬዝ እንዳለው ከልጅነ... ጀምሮ መምህር ሆኖ ያስተማራቸው ዘመዳቸው ከነገሡ ዠምሮ ዓቃቤ ... ተብሎ ሥልጣን ይዞ የቅርብ አማካሪና ረዳት ሆኖ ያገለገላቸው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ በአሁኑ ሰዓት ዓባይ ዳር ንጉሡ ለጥቂት በፈጣን ፈረሳቸው ... መልጡ እርሱ በአብሳግ ኑር እጅ ተማርኮ የተገደለበት ምክንያት ... የተነሣ እንደ ንጉሡ የፈረሱን ልባብ ለቆ ሽምጥ ለመጋለብ ባለመቻሉ ... ቃቤ ሰዓትነቱ ደረጃ የለበሰው የወርቅ ካባና የሐር ቆብ ንጉሥ አስመስሎት ...

(1) ያጼ ልብነ ድንግል መጠሪያ ስምና ክርስትና ስማቸው ስመ መንግሥታቸው ... ተጽፎ ይገኛል ። አንዳንድ ጊዜ ወናግ ሰገድ ስም ልብነ ድንግል ስመ መንግሥት ... ልብነ ድንግል የክርስትና ስም ወናግ ሰገድ ወይም ዳዊት ስመ መንግሥት ... ትክክለኛውም ይህ የመጨረሻ ነው ።
(2) ጕለትኩ አነ ልብነ ድንግል ወስመ መንግሥትየ ዳዊት እንዘ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ... ግራ ቢትወደድ ሠርጼ ወቀኝ ሮስ (ራስ) ነቢያት ..... በየሥፍራው ተመልክቷል ።
(3) አልቫሬዝ በነአቶ ግርማ በሻህ ትርጓሜ ገጽ 167 - 168

ISIC

ሌን ፤ ለአማራ ግዛት ገራድ ሲሙን (ስምዖንን) ሾሞ እንደነበረ እናስታውሳለን ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ በደዋሮ ክርስቲያኖቹ ከያለበት ተጠራቅመው ገራድ ሲዲቅን እንዳይወጉት ስለፈራ ሲድ መሐመድን ፣ ኤሚር ሁሴን ኤል ጋቱሪን ፣ ፈራቃሃም ዲንን ሰብስቦ በገራድ ሲዲቅ ላይ አደጋ እንዳይደርስበት እርዱት ብሎ እንደላካቸው ከአረጋገጠ በኋላ የዓረቡ ጸሐፊ ራሱ አህመድ ግራኝ የዓባይን ወንዝ ተሻግሮ ከጐጃም በአማራ አገር (ቤተ አምሐራ) አድርጎ ወደ ትግሬ ሄዶ ከወዚር አዶሌ ጋር መገናኘቱን ይገልጻል ። በዚህ ጊዜ በትግሬ አገር ረሀብ ተነሥቶ ስንቅ አልቆ እስላሞቹ እከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን በስንቅ ዘረፋ የተነሣ ከትግሬዎቹ ጋር ብዙ ጦርነት መደረጉን በግዢ ረገድ ያንድ አሣ (1) ዋጋ እስከ ሁለት የወርቅ ሚትቃል (2) መድረሱን እስላሞቹ ወደ ትግሬ ሲገቡ እያንዳንዳቸው ሃምሳም መቶም በቅሎ ይዘው የነበረውን ሲወጡ ግን አንዳንድ ወይም አንድ ለሁለት ብቻ መያዛቸውን ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ ከጐጃም ቤተ አምሐራ መጥቶ ከሁለት ዓመት በፊት በበዘበዘው በሐይቅ ከገዳመ እስጢፋኖስ አጠገብ ከሰነበተ በኋላ ከሐይቅ ወደ አክሱም ሄዶ ከወዚር አዶሌ ተገናኝቶ ከዚያ አዶሌ ለሠራዬ አባስን ሾሞ ልኮት ስለነበረ ተስፋ ልዑል የሚባለው እየወጋ ስለአስቸገረው አባስን ለመርዳት ግራኝ ወዚር አዶሌን ወደ ሠራዬ መላኩን ፤ በሠራዬ የተስፋ ልዑል ዘመድ ቴዎድሮስ የሚባለው ወገኖቹን ከድቶ በአባስ ውስጥ ሠራዬን ተሾሞ ስለነበረ ተስፋ ልዑል ቴዎድሮስን እንደምን እንደገደለው ፣ ቀጥሎም ይኸው ተስፋ ልዑል ወዚር አዶሌ ወደሠራዬ አባስን ለመርዳት ሲመጣ በጫካ አድፍጦ እንደገደለውና በተራው ደግሞ ተስፋ ልዑል በአባስ እጅ እንደምን እንደሞተ ይጽፋል ።

የኛም ታሪክ ነገሥት እንደተለመደ ወደ ዝርዝሩ ጉዳይ ሳይገባ የወዚርን በተስፋ ልዑል እጅ መሞት የተስፋ ልዑልን ተመልሶ በአባስ መገደል ወሩን እየጠመረ እንደዚህ ሲል ይጠቅሳል ። «በዚህ ዓመት ሰኔ ፳፯ ቀን አዶሌ ሞተ ፤ የገደለውም የሠራዬው ሹም ተስፋ ልዑል ነው ። ተስፋ ልዑልንም መልሶ በሐምሌ ወር አባስ ገደለው ሌሎችም ከሠራዬ ብዙ ሰዎች ሞቱ» (3) ።

በዚህ ዓመት የሚለው ፲፭፻፳፯ ዓመተ ምሕረትን ነው ። ስለዚህ በዚሁ ዓመት በጥር ፲፩ ቀን ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል እንደታሪክ ነገሥቱ በአክሱም የጥምቀትን በዓል አክብረው እንደ ዓረብ ፋቂህ ደግሞ ጽላተ ሙሴን አሸሽተው ወደ መዘጋ ከመዘጋ ወደ ጐጃም ሲሄዱ ግራኝ እግር በግር እየተከታተለ በየካቲት ፳፪ ቀን ዓባይ ዳር ንጉሡን አድብቶ ለመያዝ ፈትኖ ሳይሳካለት ከቀረ በኋላ ግራኝ ከጐጃም

(1) ዓሣ ሲል ቁና ወይም መሥፈሪያ ወይም የመብል ዓይነት እንጂ ከባሕር የሚገኝ ዓሣ ማለቱ አይመስልም ።

(2) ሚትቃል የወርቅ ቁራጭ መገበያያ ገንዘብ ፤

(3) ወበይእቲ ዓመት አመ ፳ወ፯ ለሰኔ ሞተ አዶሌ ወቀተሎ ተስፋ ልዑል አቃጽነ ሠራዌ ወለተስፋ ልዑል ቀተሎ አባስ በወርኃ ሐምሌ ወሞቱ ብዙኃን እምሰብአ ሠርዌ (ሠራዌ ?) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92 ። Etudes sur l'histoire d'Ethiopie : René Basset ገጽ 14 - 15

በአማራ አገር እያረፈም ግራና ቀኝ አውራጃዎቹንም እየጐበኘ አክሱም ደርሶ ሳለ በዚሁ ዓመት አርበኛው ተስፋ ልዑል ከብዙ ዓመታት ዝምሮ ክርስቲያኖቹን ሲያ ስጨንቅ ፣ ሲማርክ ፣ ሲገድል የነበረውን ወዚር አዶሌን በሰኔ ፳፯ ቀን ገድሎ ሳለ በሚያሳዝን እኳኋን እርሱ ደግሞ በሐምሌ ወር በአባስ እጅ ሞተ ።

የዚህ ሁሉ ጦርነትና እሟሟት በታሪክ ነገሥት ውስጥ ዝርዝር ሐተታው ስለ ማይገኝ ዓረቡ ጽፎታልና የርሱን መጽሐፍ ከተረጐሙት ከሙሴ ሬኔ ባሴት ላይ የአ ማርኛውን ትርጉም እንደተለመደ ከዚህ እንደሚከተለው እናንብብ ።

«በሠራዬ ውስጥ ተስፋ ልዑል የሚባል አለቃ ነበር ። እርሱም ወዚር አባስ ሊወጋው በሄደ ጊዜ ከጫካ ገብቶ ተደበቀ ። የርሱ ዘመድ (የወንድም ልጅ ?) ቱድ ሩስ (ቱዎድሮስ) የሚባል በሠራዬ ከታወቁት ሹማምንት አንደኛው ወደ ወዚር አባስ መጥቶ ተገናኘ ። አዶሌም በአባስ ሥልጣን ውስጥ ቴድሮስን ሠራዬ አገር ሾመው ። ስለዚህ አባስ ባንድ ቦታ ተቀምጦ ቴድሮስ ያገሩን ሰው አይዟችሁ እያለ ለእስላሞቹ አሳመነ ።

በዚህ መካከል ተስፋ ልዑል ወደ ቴዎድሮስ ዘንድ ምንም ባልጠረጠረበት ሰዓት ሄዶ በድንገት ተዋጉና ተስፋ ልዑል ቴድሮስን ገደለው ። በዚህ ሰዓት ወዚር አዶሌ ከአክሱም ወደ ሠራዬ መንዙን ተስፋ ልዑል ስለሰማ በአባስና በወዚር አዶሌ መካከል በሚገኘው ጫካ ውስጥ ተደብቆ ማንም ሳያውቀው ጥቅጥቅ አለውና እተ ተበተበው ጫካ ውስጥ ጦሩን አከማችቶ [illegible]ብቅ ዠመር ። መንገዱም ጠባብ ከመ ሆኑ የተነሣ ወደሰፊው መንገድ ለመድረስ በዚህ ጫካ በፈረስ ማለፍ የሚቻለው አንዱ ካንዱ ኋላ ተከታትሎ ነው ። ስለዚህ ወዚር አዶሌ ወደዚህ ጫካ መግቢያ በደ ረሰ ጊዜ ‘‘መዘበራረቅ እንዳይሆን ማንም ሰው ወደፊት አይለፍ ፤ እኔ ቀድሜ እመራ ችኋለሁ’’ ብሎ ለወታደሮቹ ተናገረና ከቢር መሐመድን ፣ ገራድ ሃይጁን አስከትሎ እፊት ቀድሞ መንገዱን ሲጀምር እስላሞቹ ሁሉ ከኋላ ተቀጣጥለው ይጓዙ ዠመር። ወዚር አዶሌ ከነጓደኞቹ ወደ መካከል ሲገባ በጫካ የተደበቁት የአግረኛ ወታደ ሮች ሳያስበው በድንገት በጦር እብዙ ቦታ ወግተው ጣሉት ።

በዚያን ጊዜ ጐበዙ በርበሪ የሚባለው እስላም ወደወዚር አዶሌ ሮጦ ሄዶ አነ ሣውና በዠርባው ተሸክሞ የቀስት ፍላጻ እንደ ዝናም እየወረደበት ወደኋላው መመለስ ዠመረ ። ወዚር አዶሌ እንደ ሕፃን ልጅ በዠርባው ሆኖ ‘‘ምንም የሕይ ወት ትንፋሽ የለኝምና ይልቅስ ጥለኸኝ ራስህን አድን (ሽሽ)’’ አለው ። በዚያን ጊዜ እመሬት ላይ አስቀመጠው ። እስላሞቹ ከመንገዱ መጥበብ የተነሣ ወደፊት ለማለፍ ተቸግረው ሳለ እንደበርበሪ ዠግና የሆነው ከቢር መሐመድ የአዶሌ የፈረ ሰኛ ወታደር (ጋሻ ዣግሬ) ወደፊት ቀድሞ ሳለ እንደዚሁ ተመትቶ ተገደለ ። ገራድ ሃይጁም በተራው ወደፊት ሲያልፍ እንደዚሁ ሞተ ። ገራድ ሃይጁም የባሌ ተወላጅ ነው ። የቀሩት እስላሞች እፊት የቀደሙት በዚህ ዓይነት መሞታቸውን ሲረዱት የተረፉት ወደኋላ ተመልሰው ከጫካ ወጥተው እሰፊው ሜዳ ላይ ሠፈሩ ። ክርስቲያ ኖቹ ስለሸሹ እስላሞቹ የአዶሌንና የጓደኞቹን ሬሣ አንሥተው ቀበሩና ወደ ወዚር አባስ ሄዱ ። በዚህም ሰዓት የእስላሞቹ መሪ ፋራ ቃሃም አሊ ስለነበረ የአዶሌን

የዓቃቤ ሰዓቱ ደረጃ በአስተዳደር በፍርድ በምክር ከቢትወደዶቹና ከራሶቹ በላይ ከንጉሡ በታች መሆኑን ያሳያል ። የራስና የቢትወደድ ደረጃ በዚህ ጊዜ እንደዛሬው በትክክል የተለየ አይመስልም ። ባንድ ቦታ ላይ የግራ ወይም የቀኝ ቢትወደድ ያለ ውን ያንኑ ሰው በሌላ ቦታ ራስ ይለዋል ። ይህ የዓቃቤ ሰዓት ከፍተኛ ደረጃ ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን በዚህ ዓይነት ሲታይ «ሌሎች ነገሥታት አፈረሱት» እንዳ ለው በጐንደር ዘመነ መንግሥት የዓቃቤ ሰዓቱ ደረጃ ወደታች ዝቅ ብሎ ከአክሱም ንቡረዕድ በላይ ከታላቅ ብላቴን ጌታ በታች መሆኑን ያዔ በካፋ ዜና መዋዕል ያመለክታል (ጉይዲ ያሳተመው ኮርፑስኮ ያደሰው ገጽ ፬፻ ፺፫) ወደ መጨ ረሻ ደግሞ እያደር ተዳክሞ ከሁሉም ዝቅ እያለ መጥቶ እስከመጥፋት ደርሷል ።

ስለዚህ አሁን አብሳማኑር ንጉሡን ያገኘ መስሎት በፈረስ አባሮ ይዞ ንጉሥ አለመሆኑን ካወቀ በኋላ የገደለው ዓቃቤ ሰዓቱ የመጠሪያ ስሙ ነገደ ኢየሱስ መሆ ኑን የሚያስረዳን ዓዔ ልብነ ድንግል ለአክሱም ጽዮን ፤ ለአምባ ሠነይት ወይም ለነ ሮቤል ጉልት እየጐለቱ እሰጡበት ጽሑፍ ላይ ብዙ ጊዜ የርሱን ስም ከርሳቸው ስም እየቀጠሉ ጽፈውታል (1) ። አንዳንድ ጊዜ ከራሳቸው የባለቤታቸውን የወናግ ሞገ ሳን (ሰብለ ወንጌል) እንደዚሁም ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ የገቡ እንደሆነ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ፫ኛ ደረጃን ይይዛል (2) ።

ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ፖርቱጋሎቹ ከአሥር ዓመት በፊት የመጡ ጊዜ እየተቀበለ ያነጋገራቸው ፤ ከብዙ ቀን ደጅ ጥናት በኋላም ወደ ንጉሡ አቅርቦ ያገና ኛቸው እርሱ ነው ። ብዙ ጊዜ ከዚህ በፊት ስሙን ደጋግመን ያነሣነው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ወዳገሩ ገብቶ በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፉ ላይ ስለዚሁ ስለ ዓቃቤ ሰዓት እንደዚህ ይላል «ትልቅ የሐር ቀብ የሜነ የንጉሡ ነገሥቱ መምህርና ዘመድ ነው የሚሉት አንድ ሽማግሌ ወደኛ መጣ ። ይህ ሰው ዓቃቤ ሰዓት በሚያ ሰኝ የማዕርግ ስም የሚጠራ በአገሩ ውስጥ ያለ ሁለተኛ ታላቅ ሰው ነው» (3) ።

በዚህ ዓይነት ከብዙ ዘመናት ምናልባት አልቫሬጽ እንዳለው ከልጅነታቸው ጀምሮ መምህር ሆኖ ያስተማራቸው ዘመዳቸው ከነገሡ ዠምሮ ዓቃቤ ሰዓት ተብሎ ሥልጣን ይዞ የቅርብ አማካሪና ረዳት ሆኖ ያገለገላቸው ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ በአሁኑ ሰዓት ዓባይ ዳር ንጉሡ ለጥቂት በፈጣኑ ፈረሳቸው ጋልበው ሲያ መልጡ እርሱ በአብሳማ ኑር እጅ ተማርኮ የተገደለበት ምክንያት ከሽምግልናው የተነሣ እንደ ንጉሡ የፈረሱን ልባብ ለቆ ሽምጥ ለመጋለብ ባለመቻሉ ወይም በዓ ቃቤ ሰዓትነቱ ደረጃ የለበሰው የወርቅ ካባና የሐር ቀብ ንጉሥ አስመስሎት ባንደ

(1) ያዔ ልብነ ድንግል መጠሪያ ስምና ክርስትና ስማቸው ስመ መንግሥታቸው ብዙ ጊዜ እየተቀያየረ ተጽፎ ይገኛል ። አንዳንድ ጊዜ ወናግ ሰገድ ስም ልብነ ድንግል ስመ መንግሥት አንዳንድ ጊዜ ልብነ ድንግል የክርስትና ስም ወናግ ሰገድ ወይም ዳዊት ስመ መንግሥት እየተባለ ተጽፏል ፤ ትክክለኛውም ይህ የመጨረሻ ነው ።
(2) ጐለትኩ እነ ልብነ ድንግል ወስመ መንግሥትየ ዳዊት እንዘ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ እንዘ ግራ ቢትወደድ ሠርፄ ወቀኝ ሮስ (ራስ) ነቢያት . . . . . በየሥፍራው ተመልከት ።
(3) አልቫሬጽ በነአቶ ግርማ በሻህ ትርጓሜ ገጽ 167 - 168

ኛው ወይም በሁለቱም ምክንያት ይሆናል ።

በዚህ ቀን አብሮ ስለሞተው ስለብእሴ እግዚአብሔር የዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ልጅ ከመሆኑ በቀር ምንም የምናውቀው የለም ። ዓረብ ፋቂህም አያወሳውም። ቀኝ ጌታ ወሰንጌ የሚባለው ሌላ ዝርዝር ነገር ሳይሰጥ በዚህ ቀን ከሌሎች ጋር መሞቱን ታሪከ ነገሥቱ መጥቀሱን እንብበናል ።

እንደ ዘመኑ የአሿሿም ልማድ ቀኝና ግራ የሌለው ነገደ ኢየሱስ ዓቃቤ ሰዓት በነበረበት ሠርጌ ግራ ቢትወደድ በድሌ (በድላይ) የቀኝ ቢትወደድ ፤ ዕንቊ ሐዋርያት የግራ ሕዱግ ፣ ራስ ፋኑኤል የቀኝ ሕዱግ ፣ ራስ ደገልሃን የግራ አዛዥ ፣ ይስሐቅ የቀኝ አዛዥ ተብለው በተጠቀሱበት ባንድ ቦታ ተስፋ ኢየሱስ የሚባል የግራ ጌታ ሆኖ ሳለ ወሰንጌ የቀኝ ጌትነቱን ሥፍራ ይዞ ነበር (1) ።

ቀኝ ጌታና ግራ ጌታ የሚባለው ሹመት ዛሬ በቤተ ክህነት ብቻ በአንድ ደብር ውስጥ ከአለቃቸው በታች ከርዕሰ ደብር ቀጥሎ የሚሰጥ የቤተ ክህነት ሹመት ሆኖ ቀርቷል (2) ። በዚያን ጊዜ ግን በቤተ ክህነት ሥልጣኑ ላይ ከአዛዦቹ ወይም ከቃለ ሐዬዎቹ ጋር እየተጐራበተ በአስተዳደር ወይም በፍርድ እየገባ የሚያስተዳድር ይመስላል ። ያለዚያ ወሰንጌ ከታላላቆቹ ካያላን ከነቢትወደድ ሠርፄ ከነአዛዥ ደገልሃን ጋር ከታሪካዊ ጽሑፍ ዝርዝር ገብቶ በንጉሡ አንደበት ለምስክርነት በጽሑፍ የመወሳት መብት ባላገኘ ነበር ።

ISIC

ምዕራፍ ፹፮

የወዚር አዶሌ በሠራዬ ሹም በተስፋ ልዑል እጅ መሞት (፲፰፻፷፯ ሰኔ ፳፯ ቀን) ፣
የተስፋ ልዑል በወዚር አባስ እጅ መሞት (ሐምሌ)

ዓፄ ልብነ ድንግል በፈረስ አምልጠው ዓባይን ተሻግረው ጐጃም ከገቡ ወዲህ ጥንቃቄና ጀግንነት በየመልኩ ሁለት ባሕርይ አድርጎ የያዘው ግራኝ አህመድ የተያዙትን አውራጃዎች ያሉበትን ሁኔታ እየመረመረ ሳያረጋግጥ እርሳቸውን በጭፍኑ እግር በእግር መከታተሉ እንደማይጠቅመው ተገንዝቦታል ። ተንኮልና ጥንቃቄ ዠግንነቱም በርሱ አካል ተዋሕደው አንድ ባሕርይ ስለሆኑ አዋሕዶም ሠልሶም እንደ አስፈላጊነቱ ሲሠራባቸው ይታያል ።

እርሱ ወደትግሬ ሲዘምት አምና ለደቡቡ ግዛት በተለይ በደዋሮ በኤሚር ሁሴን ውስጥ ገራድ ሲዲቅን ሾሞ መምጣቱን ፤ ከትግሬ በተለይ ከአክሱም ንጉሡን ለመከታተል በጸለምት አድርጎ ወደ መዘጋ የዘመተ ጊዜ ለትግሬ ግዛት ወዚር አዶ

(1) በእኩቴተ እብ . . . . . ሠራዕክዎ ለሊቃናስ እን ንጉሥ ወናግ ሰገድ በዣን ጽጌ ዘውእቱሙ ሰብእ ሰዓታት ዘገበዘ አክሱም እንዘ ሀሎኩ በምድረ መሐሽ . . . . . . እንዘ ዓቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ ወግራ ቢትወደድ ሠርጼ . . . . . . እንዘ ግራ ጌታ ተስፋ ኢየሱስ ወእንዘ ቀኝ ጌታ ወሰንጌ ወበዓለ መጽሐፍ ሀኖ . . . . . ገበዘ አክሱም ።

(2) ዝክረ ነገር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ገጽ 671 - 672

ሌን ፤ ለአማራ ግዛት ገራድ ሲሙን (ስምዖንን) ሾሞ እንደነበረ እናስታውሳለን ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ በደዋሮ ክርስቲያኖቹ ከያለበት ተጠራቅመው ገራድ ሲዲቅን እንዳይወጉት ስለፈራ ሲድ መሐመድን ፥ ኤሚር ሁሴን ኢል ጋቱሪን ፥ ፈራቃሃም ዲንን ሰብስቦ በገራድ ሲዲቅ ላይ አደጋ እንዳይደርስበት እርዱት ብሎ እንደላካቸው ከአረጋገጠ በኋላ የዓረቡ ጸሐፊ ራሱ አህመድ ግራኝ የዓባይን ወንዝ ተሻግሮ ከጐጃም በአማራ አገር (ቤተ አምሐራ) አድርጎ ወደ ትግሬ ሄዶ ከወዚር አዶሌ ጋር መገናኘቱን ይገልጻል ። በዚህ ጊዜ በትግሬ አገር ረሀብ ተነሥቶ ስንቅ አልቆ እስላሞቹ እከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን በስንቅ ዘረፋ የተነሣ ከትግሬዎቹ ጋር ብዙ ጦርነት መደረጉን በግዢ ረገድ ያንድ አሣ (1) ዋጋ እስከ ሁለት የወርቅ ሚትቃል (2) መድረሱን እስላሞቹ ወደ ትግሬ ሲገቡ እያንዳንዳቸው ሃምሳም መቶም በቅሎ ይዘው የነበረውን ሲወጡ ግን አንዳንድ ወይም አንድ ለሁለት ብቻ መያዛቸውን ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ ከጐጃም ቤተ አምሐራ መጥቶ ከሁለት ዓመት በፊት በበዘበዘው በሐይቅ ከገዳመ እስጢፋኖስ አጠገብ ከሰነበተ በኋላ ከሐይቅ ወደ አክሱም ሄዶ ከወዚር አዶሌ ተገናኝቶ ከዚያ አዶሌ ለሠራዬ አባስን ሾሞ ልኮት ስለነበረ ተስፋ ልዑል የሚባለው እየወጋ ስለአስቸገረው አባስን ለመርዳት ግራኝ ወዚር አዶሌን ወደ ሠራዬ መላኩን ፤ በሠራዬ የተስፋ ልዑል ዘመድ ቴዎድሮስ የሚባለው ወገኖቹን ከድቶ በአባስ ውስጥ ሠራዬን ተሾሞ ስለነበረ ተስፋ ልዑል ቴዎድሮስን እንደምን እንደገደለው ፥ ቀጥሎም ይኸው ተስፋ ልዑል ወዚር አዶሌ ወደሠራዬ አባስን ለመርዳት ሲመጣ በጫካ አድፍጦ እንደገደለውና በተራው ደግሞ ተስፋ ልዑል በአባስ እጅ እንደምን እንደሞተ ይጽፋል ።

የኛም ታሪክ ነገሥት እንደተለመደ ወደ ዝርዝሩ ጉዳይ ሳይገባ የወዚርን በተስፋ ልዑል እጅ መሞት የተስፋ ልዑልን ተመልሶ በአባስ መገደል ወሩን እየጨመረ እንደዚህ ሲል ይጠቅሳል ። «በዚህ ዓመት ሰኔ ፳፯ ቀን አዶሌ ሞተ ፥ የገደለውም የሠራዬው ሹም ተስፋ ልዑል ነው ። ተስፋ ልዑልንም መልሶ በሐምሌ ወር አባስ ገደለው ሌሎችም ከሠራዬ ብዙ ሰዎች ሞቱ» (3) ።

በዚህ ዓመት የሚለው ፲፭፻፳፯ ዓመተ ምሕረትን ነው ። ስለዚህ በዚሁ ዓመት በጥር ፲፩ ቀን ንጉሠ ዓፄ ልብነ ድንግል እንደታሪከ ነገሥቱ በአክሱም የጥምቀትን በዓል አክብረው እንደ ዓረብ ፋቂህ ደግሞ ጽላተ ሙሴን አሸሽተው ወደ መዘጋ ከመዘጋ ወደ ጐጃም ሲሄዱ ግራኝ እግር በግር እየተከታተለ በየካቲት ፳፱ ቀን ዓባይ ዳር ንጉሡን አድብቶ ለመያዝ ፈትኖ ሳይሳካለት ከቀረ በኋላ ግራኝ ከጐጃም

(1) ዓሣ ሲል ቁና ወይም መሥፈሪያ ወይም የመብል ዓይነት እንጂ ከባሕር የሚገኝ ዓሣ ማለቱ አይመስለኝም ።

(2) ሚትቃል የወርቅ ቁራጭ መገበያያ ገንዘብ ፤

(3) ወበይእቲ ዓመት አመ ፳ወ፯ ለሰኔ ሞተ አዶሌ ወቀተሎ ተስፋ ልዑል አቃጽን ሠራዌ ወለተስፋ ልዑል ቀተሎ አባስ በወርኃ ሐምሌ ወሞቱ ብዙኃን እምሰብእ ሠርዌ (ሠራዌ ?) ታሪክ ነገሥት ገጽ 92 ። Etudes sur l'histoire d'Ethiopie : René Basset ገጽ 14 - 15

በአማራ አገር እያረፈም ግራና ቀኝ አውራጃዎቹንም እየጐበኘ አክሱም ደርሶ ሳለ
በዚሁ ዓመት አርበኛው ተስፋ ልዑል ከብዙ ዓመታት ዝምሮ ክርስቲያኖቹን ሲያ
ስጨንቅ ፣ ሲማርክ ፣ ሲገድል የነበረውን ወዚር አዶሌን በሰኔ ፳፯ ቀን ገድሎ ሳለ
በሚያሳዝን አኳኋን እርሱ ደግሞ በሐምሌ ወር በአባስ እጅ ሞተ ።

የዚህ ሁሉ ጦርነትና አሟሟት በታሪክ ነገሥት ውስጥ ዝርዝር ሐተታው ስለ
ማይገኝ ዓረቡ ጽፎታልና የርሱን መጽሐፍ ከተረጐሙት ከሙሴ ረኔ ባሴት ላይ የአ
ማርኛውን ትርጉም እንደተለመደ ከዚህ እንደሚከተለው እናንብብ ።

«በሠራዬ ውስጥ ተስፋ ልዑል የሚባል አለቃ ነበር ። እርሱም ወዚር አባስ
ሊወጋው በሄደ ጊዜ ከጫካ ገብቶ ተደበቀ ። የርሱ ዘመድ (የወንድም ልጅ ?) ቴድ
ሩስ (ቴዎድሮስ) የሚባል በሠራዬ ከታወቁት ሹማምንት አንደኛው ወደ ወዚር
አባስ መጥቶ ተገናኘ ። አዶሌም በአባስ ሥልጣን ውስጥ ቴድሮስን ሠራዬ አገር
ሾመው ። ስለዚህ አባስ ባንድ ቦታ ተቀምጦ ቴድሮስ ያገሩን ሰው እይዚችሁ እያለ
ለእስላሞቹ አሳመነ ።

በዚህ መካከል ተስፋ ልዑል ወደ ቴዎድሮስ ዘንድ ምንም ባልጠረጠረበት
ሰዓት ሄዶ በድንገት ተዋጉና ተስፋ ልዑል ቴድሮስን ገደለው ። በዚህ ሰዓት ወዚር
አዶሊ ከአክሱም ወደ ሠራዬ መጓዙን ተስፋ ልዑል ስለሰማ በአባስና በወዚር አዶሌ
መካከል በሚገኘው ጫካ ውስጥ ተደብቆISTCንም ሳያውቀው ጥቅጥቅ አለውና እተ
ተበተበው ጫካ ውስጥ ጦሩን አከማችቶ ይጠብቅ ዠመር ። መንገዱም ጠባብ ከመ
ሆኑ የተነሣ ወደሰፊው መንገድ ለመድረስ በዚህ ጫካ በፈረስ ማለፍ የሚቻለው
አንዱ ካንዱ ኋላ ተከታትሎ ነው ። ስለዚህ ወዚር አዶሊ ወደዚህ ጫካ መግቢያ በደ
ረሰ ጊዜ "መዘበራረቅ እንዳይሆን ማንም ሰው ወደፊት አይለፍ ፤ እኔ ቀድሜ እመራ
ችኋለሁ" ብሎ ለወታደሮቹ ተናገረና ከቢር መሐመድን ፣ ገራድ ሃይጁን አስከትሎ
እፊት ቀድሞ መንገዱን ሲጀምር እስላሞቹ ሁሉ ከኋላ ተቀጣጥለው ይጓዙ ዠመር።
ወዚር አዶሊ ከነጓደኞቹ ወደ መካከል ሲገባ በጫካ የተደበቁት የእግረኛ ወታደ
ሮች ሳያስበው በድንገት በጦር እብዙ ቦታ ወግተው ጣሉት ።

በዚያን ጊዜ ጐበዙ በርበሪ የሚባለው እስላም ወደወዚር አዶሌ ሮጦ ሄዶ አን
ሣውና በዠርባው ተሸክሞ የቀስት ፍላጻ እንደ ዝናም እየወረደበት ወደኋላው
መመለስ ዠመረ ። ወዚር አዶሌ እንደ ሕፃን ልጅ በዠርባው ሆኖ "ምንም የሕይ
ወት ትንፋሽ የለኝምና ይልቅስ ጥለኸኝ ራስህን አድን (ሽሽ)" አለው ። በዚያን
ጊዜ እመሬት ላይ አስቀመጠው ። እስላሞቹ ከመንገዱ መጥበብ የተነሣ ወደፊት
ለማለፍ ተቸግረው ሳለ እንደበርበሪ ዠግና የሆነው ከቢር መሐመድ የአዶሊ የፈረ
ሰኛ ወታደር (ጋሻ ዦግሬ) ወደፊት ቀድሞ ሳለ እንደዚሁ ተመትቶ ተገደለ ። ገራድ
ሃይጁም በተራው ወደፊት ሲያልፍ እንደዚሁ ሞተ ። ገራድ ሃይጁም የባሌ ተወላጅ
ነው ። የቀሩት እስላሞች እፊት የቀደሙት በዚህ ዓይነት መሞታቸውን ሲረዱት
የተረፉት ወደኋላ ተመልሰው ከጫካ ወጥተው እሰፊው ሜዳ ላይ ሠፈሩ ። ክርስቲያ
ኖቹ ስለሸሹ እስላሞቹ የአዶሌንና የጓደኞቹን ሬሣ እንሥተው ቀበሩና ወደ ወዚር
አባስ ሄዱ ። በዚህም ሰዓት የእስላሞቹ መሪ ፋራቃሃም አሊ ስለነበረ የአዶሌን

ሞት ጨምሮ እንዳዘዘኸን ይኸው ወደ አባስ ዘንድ እንጓዛለን ብሎ ለይማም ደብዳቤ ጻፈለት ። ይማም በዚህ ጊዜ አባ ገሪማ አገር ላይ ነበር ። በአጠገቡ ያሉት እስላሞች ሁሉ ከወዚር ሙጃሂድ (ሙጋሂድ) ጋራ አገር ለመዝረፍ ተበታትነው ነበርና እነርሱ እስኪሰበሰቡ ድረስ እስከ ተሲያት የአዶሌን ሞት ሸሽጎ አቆየው ።

በዚህ ቀን ከሰዓት በላይ ወዚር ሙጃሂድ ከነሰዉ ወደ ሠፈር ገባ ። እብድ ኢንናስርም ከኋላው ክርስቲያኖቹ እያባረሩት ከዋድላ ተመልሶ ወደ ይማም መጣ ። ሁሉም እስላሞቹ በሙሉ ከተሰበሰቡ በኋላ ይማም ነጋሪት እያስመታ ሁሉንም በፊቱ ሰበሰበ ፤ አብዛኞቹም በቅርብ ጊዜ የሰለሙ ነበሩ ። በዚያን ጊዜ "ከይማም አገልጋዮች አንዱ አዶሌ ሞተ ። በርሱም ፈንታ አንዱ የይማም አገልጋይ ተተክቷል" የሚል ቃል በገሀድ ተነገረ ። በዚያን ጊዜ ስለወዚሩ በሠፈር ለቅሶና ኀዘን ሆነ ። ከዚህ በኋላ የወዚር አዶሌ ሹመት ለወዚር አባስ ተሰጠ ።

ተስፋ ልዑል በበኩሉ የአዶሌን ራስ ቆርጦ ወደ ዋፍላ (1) ለንጉሡ በላከ ጊዜ ንጉሡ ነጋሪትና ጥሩምባ መለከት አስነፋ ። የብረት እንደቆጥ ያለ አሠርቶ ሹሙን ደገልሃንን ውጣና ተናገር ብሎ አዘዘው ። ደገልሃንም እመናገሪያው ላይ ወጣና "እናንተ መነኩሳትና ዲያቆናት ፣ መኳንንትና ቀሳውስት አዶሌና ሌሎች ሹማምንቶች መሞታቸውን እወቁ እንግዲህ የኛ ክብር የእስላሞች ሐሣር መጀመሩን ተገንዘቡ" እያለ በው[illegible]ኤሚሮች ሁሉ እንደሞቱ አስመስሎ ተናገረ ። ነገር ግን እግዚአብሔር የርሱን ምኞት አልተቀበለውም ። ቢሆንም የሰሙት ሁሉ ደስ ብሏቸው ፫ ቀን ሙሉ ነጋሪት እየመቱ በክብር ሲዘምሩ ሲያጌጡ ሲጠጡ ሰነበቱ ። ተስፋ ልዑልም ኩራትና ትምክህት አደረበት "ወዚር አዶሌንና ሃይማኖቱን ለውጦ የሰለመውን ቴድሮስን (ቴዎድሮስን) ገደልሁ ወደፊትም የቀሩትን እጨርሳቸዋለሁ" እያለ ይናገር ጀመር ።

እንደዚህም ብሎ ወታደሩን አሰልፎ ወዚር አባስ ወደአለበት ሥፍራ ይጓዝ ጀመር ። የዚህንም ወሬ ይማም በሰማ ጊዜ ሠራዊቱን በሙሉ ይዞ ሄደና እሠራዬ ወሰን ላይ አባ ሃሌሎ (2) እሚባለው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ደረሰ ። የዚህም አገር ሕዝብ ግብራቸውን እየከፈሉ በሰላም ተቀምጠው ነበር ፤ ወዲያውም ወደ ይማም መጡና ሹሙ ተስፋ ልዑል ጦሩን አሰልፎ ወደ ወዚር አባስ ሄዶ ተዋግተው እስላሞቹ በሙሉ አንድም ሳያመልጥ ሞቱ ብለው ነገሩት ። ይኸንንም ማለታቸው ይማም ከነጦሩ ባገራቸው እንዳይሠፍር ብለው ነው እንጂ ነገሩ ውሸት ነው ። ይማም የዚህን ወሬ ሲሰማ ለወዚር አዶሌ ከአዘነው ይበልጥ ኀዘን ተሰማው ። ነገሩንም ለማረጋገጥ በአጠገቡ ወደሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ዘንድ አንድ እስላም ላከ እርሱም አንዱን መነኩሴ በጦርነቱ ላይ የነበረና ወሬ ለወገኖቹ ሊነግር የመጣ ነው ብሎ አምጥቶ እይማም ፊት አቀረበውና ቢጠየቅ "እስላሞቹ ተሸንፈዋል" ብሎ ገለጸ ።

የዚህንም ወሬ ይማም አህመድ ለአምስት ጓደኞቹ ለነኤሚር ሑሴን . . . . .

(1) በአሸንጌና በጡግና መካከል ከተማው እዲጋሎ
(2) ሃሌሎ (ሃሌሉያ) ወደፊት ከአክሱም ጽዮንና ከደብረ ብንኰል ጋር ሲቃጠሉ እንመለከታለን ።

ለነአብሳማ ኑር ፣ ለነወዚር ሙጃሂድ ብቻ ነግሮ የቀረው ሰው እንዳይሰማ ወሬውን ደበቀ ። ኢሚር ኡመርም "ለምን በዚህ ነገር ታዝናለህ ይኸው እነሆ ከ፲ ዓመት ዠምሮ በክርስቲያኖቹ አገር ሆነን ክርስቲያኖቹን እየፈጀን ፣ እየማረክን እንዘርፋ ለን" ብሎ ነገረው (አጽናናው) (1) ። ይማም ግን በዝምታ ይኸን ያለበትን አገር ለቆ ወደፊት ጉዞውን ያዘ ። ለግንባር ቀደሙም ጦር አብድ ኢን ናስርን ሾመው ። እርሱም ከዋናው ጦር ሳይርቅ ከወዚር አባስ ዘንድ የመጡ የፈረሰኛ መላክተኞች አገኘ ። እነርሱም "ሁላችንም ደህና ነን ፤ አገሩም መልካም ነው" የሚል መልእ ክት ከወዚር አባስ ለይማም የያዙ መላክተኞች ነበሩ ። ከመልክተኞቹም ውስጥ አህመድ ጎይታና ተስፋዊ የሚባል የሟቹ የቴድሮስ ወንድም ነበሩ ። እነሱም ከአ ብድ ኢን ናስር የተገናኙት በጨለማ ስለነበረ ሳይተዋወቁ በስሕተት ከጉዞ ላይ ሊዋጉ ነበር ። በኋላ ግን ንግግር ተመላልሰው በቋንቋ ከተዋወቁ በኋላ ተገናኙና ወሬ ቢጠየቁ አገሩ ደህና ነው ብለው መለሱ ። እስላሞቹም በዚሁ ሠፈር አደሩ ። ይማም ሊነጋ ሲል እዚሁ ሠፈር ከነጦሩ ደረሰ እነዚያን የሐሰት ወሬ የነገሩትን የቤተ ክህነት ሰዎች አቀረበና "በምን ምክንያት የውሸት ወሬ ነገራችሁኝ" ብሎ ቢጠይቃቸው "አጥፍተናልና ምሕረት አድርግልን" ብለው መለሱለት እርሱም ይቅርታ አድርጎ ለቀቃቸው ።

ሹሙ ተስፋ ልዑል ወደ አባስ መጓዙን በሰማ ጊዜ ይማም ቀስትና ጦር ጋሻ የያዙትን ወታደሮቹን አስልፎ በቶሎ [illegible]ወዚር አባስ ገሠገሠ ። በወታደሩም ፊት ለፊት አንድ በአህያ ተቀምጦ የሚጓዝ መነኩሴ "ዛሬ አባስን ጦርነት ብትገጥሙት ታሸንፋታላችሁ" እያለ በሐሰት ንግግር ክርስቲያኖቹን ሲያሳስታቸው ነበር ። ተስፋ ልዑልም የመነኩሴውን መልካም ንግግር ተማምኖ ከአሥራ ሦስት ፈረሰኞች ጋር እፊት እፊት በፈረስ ይጓዝ ነበር ። የእግረኛ ወታደሩ ቁጥሩ ብዙ ነበር ፣ እነሱም የሲመት አገር ሰዎች ነበሩ (2) ። ከእስላሞቹ ወገን የነበረው ጦር ፩፻ ፈረሰኛ ፣ ፳፻ የእግረኛ ጦር ነበር ። ተስፋ ልዑል ነጋሪት እያስመታ ሲጓዝ እስላ ሞቹ ሠፈር ተሰማ ። ስለዚህ ሁሉም ከየሠፈሩ ወጥቶ ለጦርነት ተሰለፈ ። ሁለቱ ወገን የጦር ሠራዊት ሲቀራረብ ሁለቱ የሹሙ (የተስፋ ልዑል) ልጆች አሮንና በለው ሰገድ ከፈረስ ወርደው የጦር ልብሳቸውን አጥልቀው ጋሻና ረዣዥም ጦራ ቸውን ይዘው "እያንዳንዳችን ከ፰ የእስላም ፈረሰኛ እንበልጣለን" እያሉ ጦራቸ ውን አሹለው ወደፊት ተጓዙ ። በውነትም በጉብዝናቸው የታወቁ ነበሩና በጦር እየ ወረወሩ መውጋት ዠመሩ ። እስላሞቹም በፈረስ ላይ ሆነው ውጊያውን መከቱ ። እየገሠገሡም በክርስቲያኖቹ ሰልፍ ውስጥ ገቡ ። በመዠመሪያ የገባው ከአለቆች አንዱ ኡሚር አቡበክር ቀጢን (ቀጭን አቡበክር) ነው ። እርሱም ጭኑን በጦር ተወጋ ። ከርሱ ቀጥሎ በርበሪ ገባ የርሱም ፈረስ ከቋንዣው ላይ ተመትቶ ወደቀ ። ከዚያ ገራድ ኡስማን ቤን ጃውሂር በክርስቲያኖቹ መካከል ገብቶ የጦር ዝናም እየ

(1) ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ከተደረገው ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዠምሮ ማለቱ ነው ።

(2) የሲምት (SIMT) ሰዎች የሚላቸው ጸለምት ይሆኑ ?

ወረደበት እየተዋጋ ሰልፋቸውን እሁለት ከፈለው ። ከርሱም በኋላ ሲዲ ኡክ ሸሪፍ
አብድራህማን ከደምቢያ ሰዎች ጋር ሆኖ ፤ ሕግ አዋቂው ሀብታ ፤ ገራድ አህመ
ዱሽ ፤ ፋራቃሃም ሳቱ ወደ ሰልፉ ገብተው ይዋጉ ዠመር ። ፋራቃሃም ኡስማን ዋና
ውን የእስላሞቹን ጠላት ሹሙን ተስፋ ልዑልን ገጠመውና ሲዋጋ አንድ እስላም
(ከኋላው) ትከሻውን መትቶ ጣለውና ገደለው ።

ተስፋ ልዑል መሞቱን ሲመለከቱ ጭፍሮቹ ሁሉ ዠርባቸውን አዙረው
ሸሹት ዠመሩ ። የእስላሞቹ የፈረሰኛና የእግረኛ ጦርም እያሳደደ ምንም መደበቂ
ያና ደንጊያ ወደሌለበት ግልጥ ሜዳ አድርሶ ሁሉንም እስከ መጨረሻ ፈጃቸው ።
መነኩሴውም በአህያው ላይ እንደተቀመጠ ተገደለ ። አባስ እንደዚህ አድርጎ የሚ
ቹን የወዚር አዶሉን ደም ተበቀለለት ። ሠራዊቱንም አሳምኖ ገዛው ። ሕዝቡም
በሙሉ ግብሩን እየያዘ ገባ ። የተስፋ ልዑልና የልጆቹ ጭንቅላትም ተቆርጦ ወደ
ይማም በተላከ ጊዜ በእስላሞቹ ሠፈር ታላቅ ደስታ ተደረገ ። ከዚህ በኋላ የሠራዊ
ግዛት በአባስ ውስጥ ለቴድሩስ ወንድም (ለተስፋዊ) ተሰጠው ። አባስም የወዚር
ነት ማዕርግ አገኘ ። በርሱም ውስጥ አፍራ የሚባለው (የክርስቲያን የጦር አለቃ
የነበረ ?) ባሕር ነጋሽ ተባለ ፤ የድሆኖ የወደብ ሹመትም ለሸሪፍ ኑር ተሰጠ» (1) ።

የወዚር አዶሌ በሠራዊ ሹም (አቃፀነ ሠራዊ) በተስፋ ልዑል እጅ መሞትና
የተስፋ ልዑል በወዚር አባስ እጅ መሞት በዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ውስጥ በዚህ ዓይ
ነት ተተርኮ ይገ[illegible] መቸም ዓረብ ሃይማኖቱ እስላም እንደ መሆኑ መጠን በው
ጊያው ላይ አንዳንድ ጊዜ የክርስቲያኖቹን ዠግንነት ቀዝቀዝ የእስላሞቹን ደመቅ
እያደረገ መጻፉ የታወቀ ነው ። በጽሑፉም ውስጥ እገሌ የሚባል የክርስቲያን
አለቃ ሲዋጋ ሞተ ነፍሱ ወደሚያሳዝነው አገር ወደ ሲኦል ትውረድ ፤ እገሌ የሚባ
ለው የእስላም የጦር አለቃ ከክርስቲያኖች ጋር ሲዋጋ በዠግንነት ሞተ ስለዚህ ስለ
ቅዱስ ጦርነት ሕይወቱን ሠዋ ነፍሱን እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎ ገነት ያግባ
ለት እያለ የግል ስሜቱን ፍቅሩንና ጠቡን መግለጹን ሁሉ ባለፈው አንብበናል ።
ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የክርስቲያኖቹን ዠግንነት ብዙ ጊዜ በማንሣቱ በታሪክ
አተራረክ ረገድ ከሐቀኝነት አይርቅም ።

ስለዚህ ተስፋ ልዑል ወዚር አዶሌን በሜካ ተደብቆ ገደለው ወዚር አባስ ግን
ተስፋ ልዑልን በሜዳ ላይ ፊት ለፊት ሲዋጋው ሌላው እስላም የተስፋ ልዑልን
ትከሻ መትቶ ገደለው እያለ በጽሑፉ ሲያሳየን በእርግጥ ታሪኩ እንደዚሁ መሆኑን
ወይም በክርስቲያኖቹ ጸሐፊዎች ዘንድ እንደማይቀረው በዓረብ ፋቂህ መንፈስ
ውስጥ ክርስቲያኑን ለማኰሰስ እስላሙን ለማግነን ያመጣው ይሁን አይታወቅም ።
ነገር ግን በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ለእስላሞቹ ኃይል ሰጥቷል ። ከደዋሮ ፤ ከሸም
ብራ ኩሬ ዠምሮ ድል ከነርሱ እጅ አልወጣም ። ስለዚህ እስላሞቹ በፊት ለፊትና
በሜዳ ጦርነት ስለማይቻሉ የተስፋ ልዑልና የወዚር አዶሌ የፊተኛው የወዚር አባ
ስና የተስፋ ልዑል የኋለኛው ጦርነት በዚሁ ዓረብ ፋቂህ በተረከው መሠረት የተ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 442 - 449

ፈጻሚ መሆን አለበት ። ይኸም ሲሆን ተስፋ ልዑል የተሻለ ጊዜና በቂ ኃይል ወደ ፊት እስኪያገኝ ድረስ ይልቁንም ራሱ ግራኝ ወደርሱ መጓዙን ሲሰማ ፊት ለፊት መግጠምን ሳይደፍር ገለል ሊል በተገባው ነበር ። ዓረብ ፋቂህ የሚለውም እውነት እንደሆነ ዛሬ አባስን ግጠሙት ታሸንፉታላችሁ ብሎ የሰበከውን የመነኩሴ ትንቢትም ባልሰማ የተሻለ ነበር ። በዚህ ፈንታ ባለፈው ጦርነት ከወዚር አዶሌ ጋር እንደ ጀመረው የድበቃ ጦርነቱን ቢቀጥል ኖሮ ምናልባት ራሱን ከሞት አቆይቶ በእስላሞቹ ላይ ብዙ ጉዳት ሳያደርግ አይቀርም ነበር ።

ዳሩ ግን የወገን ከዳተኛ ሁልጊዜ መኖሩ ካልቀረ የድበቃውም ጦርነት ከንቱ ይሆናል ። በሸዋና በደዋሮ በፈጠጋር ፤ በይፋት እነአዝማች ሃይቤ ፤ እነአናንያ ፤ እነወናግ ኀርን እነድልበ ኢየሱስ እንደነበሩ በዚህ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በሠራዊ ወገኖቻቸውን ክርስቲያኖቹን ዘመዶቻቸውን እነተስፋ ልዑልን ከድተው የግራኝን ጦር የሚያገለግሉ የራሱ የተስፋ ልዑል የቅርብ ዘመድ ቴዎድሮስና ወንድሙ ተስፋዊ የሚባሉት ናቸው ። አፍራ የሚባለውም ከነዚሁ ጋር አብሮ አለ ። በተረፈ ደግሞ ጥቅል ድምሩ የበለው ነገድ እስላሙ ሁሉ ከግራኝ ጋር ማበሩን ባለፈው ተመልክተናል ። በዚህ ምክንያት በአገር ተወላጅና በውጭ አገር ጥርቅም ጦረኛ የደረጀውን የግራኝን ጦር ፊት ለፊት ተቋቁሞ ለማሸነፍ ለሌሎቹ ያልሆነው ለአንዱ ለተስፋ ልዑል ፈጽሞ ሊሆንለት አይችልም ።

ለግራኝ አህመድ በአሁኑ ጊዜ በዚህ በሠራዊ የጦር ግንባር የጠቀመው የቤተ ዘመዳሞቹ የተስፋ ልዑልና የቴዎድሮስ መለያየት ነው ። እንደዚህ ያለውን በዘመድ መካከል መለያየትን የሚፈጥር አንዳንድ ጊዜ የርስትና የሹመት ባላንጣነት ነው ። ምናልባት ባዜ ልብነ ድንግል ፊት ተስፋ ልዑል ሞገስ አግኝቶ ሠራዊን ተሾሞ ሲከበር በዚሁ እንፃር ደግሞ የዘመድ ባላንጣው ቴዎድሮስ በቅርታ ኖሮ አሁን ያዜ ልብነ ድንግል ዕድል በአጋደለበት የግራኝ አህመድ ዕድል በተቃናበት ሰዓት የሠራዊን ሹመት ለማግኘት መፈተኑ ይሆናል ። ለሹመትም ከመጓጓት የተነሣ ለመሾም ሲል ሃይማኖቱንና ወገኖቹን ክዶ ይሆናል ። ነገር ግን ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ተስፋ ልዑል እንደገደለው ስለተመለከትን በክዳት ባገኘው ሹመት እንደ አውራይ ኡስማን ምንም ያህል አልተጠቀመም ማለት ነው ። እንደእርሱ ከዳተኛ የሆነው ወንድሙ ተስፋዊ ግን ከተስፋ ልዑል ሞት በኋላ በቴዎድሮስ ምትክ በአባስ ውስጥ የሠራዊን ግዛት መሾሙን ስናውቅ ፍጻሜውን አላገኘነውም ። ከባላንጣነት ወይም ሹመት አነሰኝ ከሚያሰኘው ኵርፊያ በቀር ደግሞ እንደዚሁ ወገኑን መክዳት ደስ የሚለው በዚህም አስከፊ ሥራ የሚደሰት በአገር ታሪክ ውስጥ ጣልቃ እየገባ ይገኛል ። ያድር ባይነት ጠባይ ያላቸው ጮሌ ሰዎች የጊዜውን የጦርነት አካሄድ እያመዛዘኑ እንኳን ተበድለው ሳይበደሉም ጊዜ ለጣለው ጀርባቸውን በመስጠት ጊዜ ላነሣው ፊታቸውን መልሰው የሚያገለግሉ እሉና የቴዎድሮስና የወንድሙ የተስፋዊ ክዳት በየትኛው ዓይነት መሆኑን ከዚህ ከሩቁ ዘመን ላይ ሆኖ ለመለየት ያስቸግራል ። የሆነ ሆኖ አገርንና ወገንን ለሚክድ ምንም ዓይነት ምክንያት ቢቀርብ በታሪክ ፊት ይቅርታ ሊያሰጥ አይችልም ። ባገር ላይ በወገን ላይ የሚፈጸ

መውን የከዳት ኃጢአት ምንም ዓይነት ምክንያት ሊያስተሠርየው አይችልም ።

የዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ የቴዎድሮስንና የተስፋዊን ከተስፋ ልዑል ጋር ያለውን ቅርብ ዝምድና ስለሚገልጽ እላይ በመዠመሪያው እንዳመለከትነው ከሌላው ምክንያት ይልቅ የባላንጣነቱ ጉዳይ ይኖር ይሆናል ብሎ ማመኑ ከሁሉ የቀረበ ነው ። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ባላንጣነት የፈጠረው ጥቃት እየገጠማቸው ባለፈው መንግሥት ከሹመት በመዋረድም በእሥራትም በግዞትም ኖረው ሳለ ወገንን የሚያመስስ ሃይማኖትን የሚያጠፉ ባዕድ የመጣ ለት ወደ ባዕድ ዞሮ የማያኮራ ግዛትና ሹመት በመፈለግ ፈንታ ያለፈ ቂማቸውን ውጠው የጦርነትን ችግርና መከራ ከወገናቸው ጋር በትእግሥት መካፈልን የሚመርጡ የታላቅነት መንፈስ ያላቸው ይገኛሉ ። እነዚህ በትክክል በዚህ ዓይነት አቅዋም በሕይወትም በሞትም ቢገኙ የክብር አክሊል የሚገባቸው ያገር ሰማዕታት ናቸው ማለት ነው ።

ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ ።

ተስፋ ልዑል የገደለው ወዚር አዶሌ ዋና የግራኝ የጦር አለቃ በእስላሞቹ ዘንድ የተከበረ መሆኑን የዚህን የግራኝንና ያፄ ልብነ ድንግልን የጦርነት ታሪክ ከሥሩ ዠምሮ ያነበበ ሰው ሁሉ በዝርዝር ያውቀዋል ። ከዚህ በፊት በሕይወቱ ጊዜ ስለርሱ የተጻፈውን አሁን በሞቱ መልሰን አንድ ጊዜ በመጨረሻ ባጭሩ እናስታውስ ። ከሥር አዶሌ የግራኝ አህመድ አባት የኢብራሂም ባሪያ ነበር ፤ በኋላ ግን ጌታው ነጻ አውጥቶት ሳለ ግራኝን ከነወንድሞቹ እንደሞግዚትም እንደአባትም ሆኖ ያሳደገ እርሱ ነው ። ወዲያው ግራኝ በአለፈው እንደተመለከትነው የሐረርን ሱልጣን አቡበከርን ገድሎ ሥልጣን በያዘ ጊዜ በዚያው አውራጃ ሲም የሚባለውን ክፍል "ሄገኖ" የሚባል የማዕርግ ስም ሰጥቶ ሾመው ። በ፲፭፻፲፱ ዓ. ምሕረት ጦርነቱ እንደተዠመረ የደዋሮን ግዛት መጥቶ ዘረፈ ባመቱ ከወናግ ዣን ጋራ ተዋጋ ። በተረፈ ግራኝ አህመድ ዋናውን ወረራ በዠመረበት ጊዜ ውስጥ አዶሌ በባደቄ ፤ በሽምብራ ኩሬ ፤ በአንጾኪያ ፤ በአይፈርስ በውስጡ ብዙ የአዳልንና የሱማሌን ጦር ይዞ እየተዋጋ ብዙ ክርስቲያኖችን የፈጀ ነው ። ግራኝ ንጉሡን ለመከታተል ወደ ቤተ አምሐራ ወደ ዋስል የዘመተ ጊዜ ወዚር አዶሌ በደቡብ ላለው ሰፋፊ አገር ዋና የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ በደብረ ብርሃን ፤ በመንዝ ፤ በዝቋላ ተቀምጦ ነበር ። ከ፯ ወር በኋላ ግራኝ ንጉሡን መማረክ አቅቶት ከዋስል ወደ ደብረ ብርሃን ከተመለሰ በኋላ በታላቅ ሰልፍ ሄዶ ከጌታው ከግራኝ ጋር መገናኘታቸውን በሥፍራው ላይ አንብበናል ። ጌታው አህመድ ግራኝ የባሌን ግዛት ሰጥቶት ወደባሌ ሄዶ ከስመ ጥሩው ጀግና ከአዝማች አዳሉ ጋር የተዋጋና በደቡቡ ክፍል ከራስ ወሰን ሰገድ በኋላ የነበረውን የመጨረሻ የክርስቲያኖቹን ተስፋ የገደለ እርሱ ነው ።

የባሌን ግዛት እያደላደለ ሲኖር በኋላ በግራኝ ትእዛዝ ወደ ደብረ ብርሃን ተጠርቶ መጣና ዘንድሮ ወደ ትግሬ እንዝመት ? ብሎ ግራኝ ሹማምንቱን ቢጠይቅ የቀሩት ዘንድሮ በዚሁ በደቡቡ ሆነን እረፍት እናድርግ ስንቅም እንሰብስብ ቢሉ እርሱ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ የለም አሁኑኑ ኃይላችን በደረጀበት ሰዓት ወደ ትግሬ መዝመትና ንጉሡንም ተከታትሎ ማጥፋት ይገባል ብሎ የመከረ እርሱ ነው ። ወደ ትግ

ሬም ከዘመቱ በኋላ አበርጋሌን ዘርፎ ግራኝ ዓፄ ልብነ ድንግልን በደምቢያና በእን ፍራዝ በኩል ሲያባርር አዶሌ መቀመጫውን አክሱም አድርጎ ትግሬ ለቀረው ለሙሉው ጦር ዋና የበላይ መሪ ነበር ። በአጭሩ አዶሌና ግራኝ እንደ ዓፄ ምኒልክና ራስ ዳርጌ ሆነው ይሠሩ ነበር ቢባል የሚመስል ነው ። ለግራኝ ምንም እንኳን በሥልጣን የበታቹና ምክትሉ ቢሆን በተረፈ አሳዳጊውና ሞግዚቱ የነበረ ስለሆነ ሌሎች ለመናገር ወይም ለመምከር የሚፈሩትን ሁሉ እርሱ ግራኝን ፊት ለፊት ለመናገርም እንዳባት ለመምከርም የሚችል ትልቅ የጦር አለቃ ነበር ። ግራኝም ትንሽ ጦር ይዞ ወደ ውጊያ ሊሄድ ሲል ፤ ወይም በጦርነቱ ግንባር ቀድሜ ልዋጋ ሲል ባባትነትና በፍቅር አይሆንም እያለ የሚቆጣ የሚመክር ያባት ሎሌ ስለነበር የርሱ ሞት በእርግጥ በተለይ ግራኝን በጠቅላላው እስላሞቹን ሊያሳዝን ክርስቲያኖቹንና ዓፄ ልብነ ድንግልን ሊያስደስት የተገባ ነው ። ዳሩ ግን በሰኔ ወር ተስፋ ልዑል አዶሌን ከገደለ በኋላ በሚቀጥለው በሐምሌ ወር ወዚር አባስ ተስፋ ልዑልን ከብዙ ጭፍራው ጋር ገድሎ ስለተበቀለ ባጭር ጊዜ ውስጥ የክርስቲያኖቹ ደስታ ወደ ኀዘን የእስላሞቹ ኀዘን ወደ ደስታ ተለወጠ ማለት ነው ። ወይም ሁለቱም ወገኖች በየተራ እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ስለሞቱባቸውና ብድር ስለተመላለሱ ደስታቸውና ኀዘናቸው የተመጣጠነ ሆኗል ለማለት ይቻላል ።

መቼም ጦርነቱ ከተዠመረ ከ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ አሁን እስከ ፲፰፻ ፳፯ ዓ. ም. ድረስ ከክርስቲያኖቹ ወገ[illegible]ደ ተስፋ ልዑል ያሉ በጣም የታወቁ ታላላቅ መሪዎች የሞቱት ብዙዎች ናቸው ። ከእነዚህም የምናስታውሰው ትግሬ መኰንን ተክለ ኢየሱስ ፤ ራስ እስላም ሰገድ ፤ ራስ ማኅፀንቶ ፤ ራስ ወሰን ሰገድ ፤ አዝማች አዳሉ ከልጁ ከመንክር ጋር ራስ ዓምዱ ፤ ተክለ ሐዋርያት ጉጅም ነጋሽ ፤ ጸሐፈ ላም ሮቤል ፤ የተጉለቱ ተክለ ጊዮርጊስ ናቸው ። ከግራኝ ወገን ደግሞ እነቢት ወደድ ሡርጌ ከአምባ ግሼን ማርከው የወሰዱት ገራድ አህሙሽ ፤ በዚያው በአምባ ግሼን የሞቱት ገራድ ማታን የሱማሌዎች አለቃ የግራኝ አማች ፤ ኰሺም አቡበክር ደዋሮ የሞተው ፤ በሻራህ በዝቋላ የሞተው ፤ በመቂት (ላስታ) በቀስት የተመታው ዘሀርቡይ መሐመድና ያሁኑ ወዚር አዶሌ ናቸው ። ቢሆንም ከሞቱት ሁሉ በደረጃውም በአገልግሎቱም አዶሌ ብልጫ አለው ።

እንደዘሀርቡይ ለአዶሌ ሞት ግራኝ ማልቀሱን ዓረብ ፋቂህ አይጠቅስም ። ምናልባት ዘሀርቡይ ወዲህ ዘመዱ ወዲህ ወጣትና ለወደፊት ዓላማ የሚጠቅመው ሆኖ ሳለ ወዚር አዶሌ ግን ምንም እንደ አባት ሎሌ ያገለገለው ቢሆን በዕድሜው የገፋ ስለሆነ በቀረው ሕይወቱ የሚሰጠው ያገልግሎት ጥቅም ያነሰ ሆኖበት ይሆናል ። ገዥና መሪ ከሁሉ በፊት ከሁሉም በኋላ የሚያመዛዝነው የአገዛዙን ጥቅም ነው ። የሆነ ሆኖ በጠቅላላው በዚህ ዘመን በተደረገው ጦርነት በአለቆችም በጭፍሮችም በኩል ከእስላሞቹ ይልቅ የክርስቲያኖቹ እልቂት እንደሚበረክት የታወቀ ነው ። በጦር ሜዳ እየተዋጋ ከሞተው ግራኝና የጦር ሹማምንቱ እያሳደዱም እየማረኩም የገደሉት ወይም አልሰልምም ሲል ያረዱት ይበልጣል ። ለመግደልና ለማጥቃት የአሸናፊና የተሸናፊ አቅም ለየብቻ እንደመሆኑ መጠን አሸናፊ በጦርነት

ሰዓት የሞተበትን ቍጥሩ ያነሰውን የወገኑን ደም ቍጥሩ በበዛው ምርኮኛ ላይ በሰበብ በአስባብ ሊበቀል ይችላል ። ጀርመኖች በ፪ኛው የዓለም ጦርነት በወረሩት በአውሮፓ አህጉር አንድ የጀርመን ወታደር ባንድ አገር አፍቃሪ እጅ ተመትቶ የሞተ እንደሆነ የርሱን ደም ለመበቀል ከደሙ ንጹሕ በሆኑት የሰላማውያን ሕይ ወት ላይ ይመልሳሉ ። በየካቲት ፲፪ ቀን ባንዱ በግራሲያኒ መቁሰል ስንት ሰው እን ደሞተ እናስታውሳለን ።

## ምዕራፍ ፹፯

## የኢትዮጵያ ንጉሥ ያዬ ልብነ ድንግል መልክተኛ አልቫሬጽ በፖርቱጋል ንጉሥ መልክተኛ በማርቲኖ አማካይነት ደብዳቤውንና ገጸ በረከቱን ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ እንዳቀረበ (እንደ አው. ቍ. ፲፭፻፴፪ ግንቦት ፳፰ ቀን)

ግራኝ አህመድ እንደዚህ አድርጎ ባዬ ልብነ ድንግል ላይ ድል በድል እያከታተለ አገራቸውን ሲወር አብያተ ክርስቲያናቱን ገዳማቱን ሲያቃጥል ሕዝቡን በሰይፍ እያስገደደ ሲያሰልም እምቢ ያለውንም በጭካኔ ሲገድል እንደ ወንድም እንደቃል ኪዳን ጓደኛ ይመለከቱት የነበረው ዮሐንስ ፫ኛ የሚባለው የፖርቱጋል ንጉሥ እን ደምኞታቸው እንኳን ተባብሮ በኢትዮጵያ ዙሪያ ዓረቦች የያዙትን አገርና ኢየሩሳ ሌምን ለማስለቀቅ ባይሞክር የራሳቸውን ነፃ ግዛት ሲቀሙ ለእርዳታ ሊደርስላ ቸው አልቻለም ።

ለርሱና ለሮማ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ ደብዳቤና ገጸ በረከት ይዘው የሄዱት ሮደሪግ ደ ሊማ ፣ አባ ጸጋ ዘአብ ፣ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ከኢትዮጵያ ከሄዱ እስከ አሁን ግራኝ ወደ ትግሬ እስከዘመተበት ጊዜ ድረስ ስምንት ዓመት ሆኗል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያንና የንጉሧን ችግር ደህና አድርገው የሚያውቁት ፖርቱጊ ዞች ይልቁንም ከሁሉ የበለጠ ኢትዮጵያዊው አባ ጸጋ ዘአብ አገሪቱ እምን ችግር ዋዜማ ላይ እንደነበረች ሲረዳው እንደምን ችላ እንዳለ በትክክል አይታወቅም ። የሆነ ሆኖ የሄደበትን ጉዳይ እንኳ ጐትጉቶ ማስፈጸም ቢያቅተው ወደ አገሩ ተመ ልሶ ባሁኑ ሰዓት ከአገር ወደ አገር ግራኝ ለሚያባርራቸው ንጉሡ ላዬ ልብነ ድን ግል አንድ መልስ ማምጣት ነበረበት ።

ነገር ግን እንኳን ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ከሊስቦን ወደሮማ ጳጳስ ዘንድ እን ኳን ሄዶ ያገሩን ወሬ ለመጠየቅ አልተነቃነቀም ። በየታሪኩ መጽሐፍ ላይ እንደ ሚገኘው ጸጋ ዘአብ ከኢትዮጵያ ሄዶ ሊስቦን በደረሰ ጊዜ የንጉሥ መላክተኛ የሚያ ገኘውን ክብር ስለአገኘ ተድላና ደስታውን እያየ የአገሩን ጉዳይ ችላ ብሏል ። እንዲ ያውም የተላከበትን ጉዳይ ወደጐን አድርጎ ካንድ ዳሚያኑስ ደ ጎኤዝ ከሚባል የፖ ርቱጋል ተወላጅ ጋር የጠበቀ ጓደኝነት ይዞ እርሱንና ዣን ደ ባሮስን የካቶሊኮቹን ባለሥልጣኖች ሁሉ ደስ ለማሰኘት ብቻ የኢትዮጵያንና የሮማን ቤተ ክርስቲያን እንድነት ፤ የወጉንና የሥርዓቱን ሁሉ ተመሳሳይነት በሐሰት እያስረዳ ወሬውን ስለ

ሰጠ ተቀባዩ ዳሚያኖስም ይኸንኑ በማመን ጽሑፉን ወደ ሮማይስጥ ተርጉሞ ለአን
ባቢ አቀረበው ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሚያውቁት እጅ
ገብቶ በተነበበ ጊዜ ሐሰተኛነቱ ስለተረጋገጠ ራሷ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ጽሑፉን
ውድቅ አድርጋዋለች (1) ።

ጸጋ ዘአብ ፲፱ ዓመት ያህል በፖርቱጋል አገር ኖሮ በመጨረሻ እንደ አውሮፓ
ቈጥር በ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. (እንደ ኢትዮጵያ ፲፭፻፴፪ ዓ. ም.) ከአልቫሬዝ ጋር ከፖር
ቱጋል አገር ወደ ሕንድ በመርከብ ሄዶ ሳለ በኋላ ኮቼን በሚባል አገር ሞቶ በቅዱስ
እንጦንዮስ (ግብጽ) ገዳም ተቀበረ ። ይኸም ዘመን ግራኝ ትግሬን ጐጃምንና
ቤገምድርን ሁሉ ወርሮ ሥልጣኑን በሙሉ ኢትዮጵያ የዘረጋበት ጊዜ ነው ። ጸጋ
ዘአብ አገሩ ወዴት እንደሆነ አይታወቅም ፤ እርሱ ግን ለመከበር ብሎ ይሁን በእር
ግጥ ይሁን አይታወቅም የቡግና (ላስታ ውስጥ) አገረ ገዥ ወይም የንጉሥ እንደራ
ሴና ሊቀ ካህናት ነኝ ብሎ ለነዳሚያኑስ መናገሩ ተጽፏል ። ሊቀ ካህናት መሆኑንና
በመጠኑ የላቲንና የጣልያን የፖርቱጋል ቋንቋ ማወቁን አልቫሬዝ በመጽሐፉ
መስክሯል ። ለመላክተኝነት ያስመረጠውም ይኸው ነው ፤ ወደ ፖርቱጋልም
ከዚህ በፊት የሄደ ይመስላል (2) ።

የሆነ ሆኖ ምንም እንኳን ጸጋ ዘአብ ቸል ቢል የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ
፫ኛና የሮማ ሊቀ ጳጳስ ቀሌምንጦስ ፯ኛ ባለፈው እንደተመለከትነው ለዝምድና
ውና ለቃል ኪዳኑ ዓፄ ልብነ ድንግል የተጉበትን ያህል አልተጉበትም ። ያልተጉበ
በት ምክንያት ብዙ ሊሆን ይችላል ። ከመዠመሪያው ላይ ደጅ ጥናት የበዛባቸው
እና ሮደሪግ ደሊማ መጥፎ ራፖር አቅርበው ይሆናል ። በዚህ ላይ ደግሞ በሩቅ ከም
ትገኘው ከኢትዮጵያና ከንጉሷ ከዓፄ ልብነ ድንግል ይበልጥ በቅርብ የሚያሳስባ
ቸው ያውሮፓ የፖለቲካና የሃይማኖት የጦርነትና የሰላም ጉዳይ ስለአለባቸው ነገ
ሩን በትኩሱ ተቀብለው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የቃል ኪዳን ጓደኝነት አድር
ገው የቱርክንና የእስላምን መንግሥታት ግብጽን ዓረብን ፤ ሁሉ ሊወጉ አልቻ
ሉም ። በዚህም ላይ አልቫሬዝና ጸጋ ዘአብ በሄዱበት ጊዜ እወሰን ላይ እነፋኑኤል
ከመዋጋት በቀር ግራኝ ኢትዮጵያን እንዳሁኑ አለመውረሩ የታወቀ ነው ። መው
ረር ከዠመረ ወዲህ ከነአልቫሬዝ ቀጥሎ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መልክተኛ ወደ ፖር
ቱጋልና ወደሮማ አልተላከም ። የወረራው ወሬም የስሚ ስሚ ቢሰማ ከሊስቦንና
ከጎአ (ሕንድ) ርቆ በሚገኘው በኢትዮጵያ መንግሥትና በአዳል ሡልጣን መካከል
የሚደረገው ጦርነት ከብዙ ዘመን ዠምሮ እንደቆየና እንደተለመደ ነገር ተመልክ
ተው በነገሩ አልደነገጡበትም ይሆናል ። ደግሞ በዚህ ላይ የፖርቱጋል ንጉሥ አብ
ዛኛ ጊዜ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚመለከተው በእንደራሴው በሕንዱ ገዥ አማካይ
ነት ስለሆነ እንደራሴው ጉዳዩን ሲያቀዘቅዘው ሊቀዘቅዝ ሲያጋንነው ሊጋነን የሚ

(1) ታሪካዊ ጉዞ ወደ አበሻ ዠሮም ሎቦ ገጽ 291 - 292 ። የፖለቲካና የሃይማኖት ታሪክ ዣ. ባ.
ኩልቦ ፪ኛ ቮሊዩም ገጽ 108 - 109

(2) አልቫሬዝ . . . . . . . ምዕ. 46 ገጽ 100 ። ምዕ. 116 ገጽ 308

ችል ነገር ነው ። እንደራሴውም በበኩሉ በዚያው በሕንድ አገር በቅርብ የሚያሳስ በው የጦርነት የኤኮኖሚ ያስተዳደር ጉዳይ ስላለበት ስለኢትዮጵያ በጥብቅ ማሰብ ያዳግተዋል ።

ጉዳዩ ከመቀዝቀዙ የተነሣ ከኢትዮጵያ ከሄዱ ስምንት ዓመት ሊስቦን ከደረሱ ስድስት ዓመት የሆናቸው የኢትዮጵያ መልክተኞች እነፍራንቼስኮ አልቫሬዝ በአ ሁኑ ጊዜ እንደ ኤው. ቍጥር ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. (እንደ ኢት. ፲፭፻፳፯ ዓ. ም.) ከሊስ ቦን ወደ ቦሎኝ (ኢጣሊያ) ሄደው ከዓፄ ልብነ ድንግል የተላከውን የወርቅ መስቀ ልና ደብዳቤ ለጳጳሱ ለቀሌምንጦስ ሲያቀርቡ እንመለከታለን ። ከዚህ ቀደም አድር ገን ሊቀ ጳጳሱ ቀሌምንጦስ በቦሎኝ የተገኙበትን ምክንያት እንጠቅሳለን ።

በዚህ ዘመን በአውሮፓ ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ሻርል ፭ኛ የሚባል ስመ ጥር ንጉሥ ተነሥቶ ነበር ። እርሱም የቆንገ'ው ፊልጶስ የእትሪሽ መሥፍንና የእብዲቱ የግን ደካስቲይ (ኤስፓኝ) ንግሥት ልጅ ነው ። ከነዚህ ከሁለቱ የነገሥ ታት ዘር በመወለዱም በራሱም ኃይልና ትጋት ጭምር እንደ እው. ቍ. በ፲፭፻ ፲፮ ዓ. ም. የኤስፓኝ ንጉሥ ከተባለ በኋላ ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ ቀጥሎ በአሉት ዓመቶች ውስጥ በኦትሪሽ ፤ በጀርመን ፤ በፍላንድር (የዛሬው ቤልዥክ) አገሮች ላይ ነገሠና መጨረሻውንም የዓለም ንጉሠ ነገሥት መባል ይገባኛል የሚል ምኞት ስለአደረበት የፈረንሳዊን ግዛት ከፍራንሷ ፩ኛ ለመቀማት ቢኮክ ፤ ፖቪ ፤ በሚባ ለው ሥፍራ ላይ እየወጋ ንጉሡን ሳይቀር ማርኮ ብዙ ግዛት ወስዶበት ሰሜን አፍሪ ካንም የራሱ ግዛት ለማድረግ ከቱርኮች ጋር በቱኒዝ ፤ በአልዠሪ ጦር እየላከ ራሱም ሄዶ አልቀናው ብሎ ሲመለስ ተናዶ ዘውዱን ከእ የታደለ መስፍን እንዳለ ይሸከ ምሀ" ብሎ ወደ ባሕር መወርወሩን ከዚህ በፊት ጽፈናል ። ይሁን እንጂ በአውሮፓ ብዙ መንግሥታትን በውስጡ አስገብሮ ሮማን ጭምር ስለያዘ እንደጥንት ሮማው ያን ደንብ "ቄሣር" ተብሎ ዘውድ ለመጫን አሰበ ። ይኸን ምኞቱን ለመፈጸም ሊቀ ጳጳሱ ለፈረንሳዩ ንጉሥ ለፍራንሷ ፩ኛ በማገዝ እምቢ ብለውት ቆይቶ ሻርልም በጳጳሱ ላይ የሮማን ሊቀ ጳጳስ ወግና ሥነ ሥርዓት በፍትሐትና በንስሐ የሚቀበሉ ትን ነቅፈው የተነሡትን ሉተርንና ተከታዮቹን እየደገፈ በሮማም ከተማ ወታደሮ ቹን እየለቀቀ ሲያዘርፍ ቆይቶ ነበር ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ የቱርኩ ሱልጣን በያለበት በአውሮፓም በአፍሪካም እየወጋ በክርስቲያን አገሮች ላይ በጣም ስለተ ጫነና ለክርስትና አቅዋም አስጊ ሁኔታ ስለፈጠረ ሊቀ ጳጳሱ የቀድሞ አሳባቸውን ለውጠው ከሻርል ጋር ባለው ጠብ ምክንያት ከሶሊማን ጋር ተስማምቶ የነበረውን ፍራንሷን ከሶሊማን ጋር ውሉን አፍርሶ ከክርስቲያኑ ከሻርል ፭ኛ ጋር እንዲስማማ አደረጉ ። ራሳቸውም እስከዚህ ድረስ እምቢ ብለው ያቆዩትን አሁን ግን በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ላይ (1) ጳጳሱና ሻርል ፭ኛ እርቅ አድርገው ጳጳሱም በዚች ቦሎኝ በምት

(1) ኩልቦ ፲፭፻፴ ዓ. ም. ላይ ሲያደርገው በፍጹም ተሳስቷል ። ምክንያቱም የዮሐንስ ደብዳቤ ለጳ ጳሱ የተጻፈው ፲፭፻፴፮ ዓ. ም. ግንቦት ፳፰ ቀን ነው ። ፪ኛ ቮሉም የኩልቦ መጽሐፍ ገጽ 107

ባል ከተማ ለሻርል ፭ኛ የንጉሠ ነገሥትነት (የቄሣርነት) ዘውድ ጫኑለት ። በዚህ ቀን በኢጣልያ አገር በቦሎኝ ስለዚህ ስለቄሣርነት ንግሥ በሻርል ፭ኛና በሊቀ ጳጳሱ መሪነት በተዘጋጀው ትልቅ በዓል ለመገኘት ከየአውራጃው ለበዓሉ የተሰበሰ ቡት መሣፍንትና መኳንንት ሊቃውንት ብዙ ስለነበሩ በዓሉ የደመቀ ሆኖ ውሏል ።

በዚሁ ስብሰባ ላይ ስለሥርዓተ ንግሡ ብቻ ሳይሆን እላይ እንዳመለከትነው የቱርክ ሡልጣን ኃይሉ በጣም እየበረታ በመሄዱ ኢየሩሳሌምንና ግብፅን ከወዲህም የአውሮፓን የባልካንን አገር ሁሉ እየወረረ ስለያዘና የክርስቲያንን ሃይማኖትም ሊገለብጥ ነው ተብሎ ሥጋት ነበርና ቱርክን ለመቃወም ክርስትናን ለመጠበቅ ያንድነት ጉራ ለማጽናት ንግግር ለማድረግ ሊቀ ጳጳሱና አዲሱ ቄሣር አሰቡ ። ስለዚህ ቱርክ ጠቅላላውን የክርስቲያንን አገር ቢያስፈራ በበኩሉ ሻርል ፭ኛ በአውሮፓ ፈረንሳዊን በቀጥታ ስለአስፈራ የፈረንሳዊ ንጉሥ ፍራንሷ ፩ኛና የቱርክ ሡልጣን ሶሊማን ትልቁ የቃል ኪዳን ጓደኛ ሆነው ቆይተው የነበረው በዚህ ጊዜ ተለዋውጦ አዲስ መልክ አበጅቶ ክርስቲያኖቹ እስኪውን የቱርክ ኃይል ለመቃወም አዲስ ጉራ አበጁ ።

የኛ መንግሥት ለዕርዳታ ተስፋውን የጣለበት የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ በዚህ በዓል ስለርሱ ሆኖ እንዲያከብር ወኪል አድርጎ የላከው ዶም ማርቲኖ የሚባለውን የቅርብ ዘመዱን ነበር ። በዚሁ ጊዜ ከኢትዮጵያ እንደ አው. ቍጥር በ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. የሄደው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መላክተኛ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ከዓፄ ልብነ ድንግል ለሊቀ ጳጳሱ የተላከውን ደብዳቤና የወርቅ መስቀል ይዞ ከዶም ማርቲኖ ጋር አብሮ ሆኖ በዚህ ጊዜ ከሊስቦን ወደ ኢጣልያ አገር መጡ ። ጸጋ ዘአብን ግን ንጉሡ በደብዳቤው እንደገለጸው በቤተ መንግሥቱ አስቀርቶት ነበር ። ቀድሞውንም ከኢትዮጵያ ሲነሡ ጸጋ ዘአብ ወደ ዮሐንስ ፫ኛ አልቫሬጽ ወደ ሮማ ጳጳስ ተልከው ነው የሄዱት ።

የሆነ ሆኖ የፖርቱጋል ንጉሥ የዮሐንስ ፫ኛ ዋና መላክተኛ ዶም ማርቲኖ ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤልና ለራሱም ለዮሐንስ የላኩትን ደብዳቤ ጨምሮ ከሸኘው ከንጉሡ ከዮሐንስ ደብዳቤ ጋር እያይዞ እንደዘመኑ ልማድ በፍርሃት እጅ ነሥቶ ለትልቁ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ አቀረበ ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለአማኑኤልና ለዮሐንስ የጻፉትን ደብዳቤዎች ከዚህ ቀደም ስለተመለከትን አሁን የፖርቱጋል ንጉሥ ከነዚሁ ደብዳቤዎች ጋር እንደ አባሪ አድርጎ ለሊቀ ጳጳሱ የላከውን የራሱን ደብዳቤ ትርጉም እንመልከት ። ባለፉትም ደብዳቤዎች ባሁኑም በወደፊቱም ትርጉም ውስጥ የታጠረው ቃል እኔ ነገሩን ለማብራራት ያገባሁት መሆኑን የቀረው ትክክለኛው የጥንቱ ቃል መሆኑን ለአንባቢ አስቀድሜ አስገነዝባለሁ ።

«የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ የላከው እክ ባሪውና ታዛዡ ልጁ ዮሐንስ በእግዚአብሔር ፈቃድ የፖርቱጋልና የአልጋርብ (ደቡብ ፖርቱጋል) ከዚያም አልፎ የአፍሪካ ባሕር ንጉሥ የጉይኔ እስከ ሕንድ ድረስ ከፋርስ እስከ ዓረብያ እስከ ኢትዮጵያ እየተጓዘ የሚገዛው የመርከብ ጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ ቅዱስ አባት በአምላካዊ ፈቃድም በዓለም የሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አለቃ ለሆነው ለቀሌምንጦስ ፲፫ኛ ዘለዓለማዊ ደስታ ይሆንለት ዘንድ ይመኛል ።

ጌታዬና አባቴ ሆይ እስካሁን በወሬ ዝናቸውን የምንሰማው በሩቅ አገር የሚገኙት ሕንድና ኢትዮጵያ እኛ ወዳለንበት የክርስትና ማኅበር ይገቡ ዘንድ በጥብቅ እነሱን እየፈለጉ ማግኘትና መሳብ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ለክርስትና አንድነት የሚጠቅም መሆኑን ዘወትር አስባለሁ ። ይኸን የመሰለው አሳብ ከሕሊናዬ ሁል ጊዜ እንዳለ ሳላስበው በእግዚአብሔር ፈቃድ የፖርቱጋልን ዘውድ ከደፋሁ ወዲህ የአረመኔዎቹን አገር ብዙ ደሴት እየፈለጉ እንዲያገኙ የጦር አለቆቹን የሚያስፈልገውን መሣሪያ እያስያዝሁ በመርከብ በያለበት በመላክ የተቻለኝን ሁሉ አደረግሁ ። እንደዚህም መጣሬ በእነዚህ አገሮች የሚገኙትን አረመኔዎችና አሕዛብ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለማምጣት ምናልባትም በየባሕሩ ጠረፍና በየአገሩ በክርስቶስ የሚያምን ሕዝብ እንዳለ ለመመርመር እንጂ ለሌላ ጉዳይ አይደለም ። እግዚአብሔር አሳባችንን ፈጽሞ አስደስቶ የጕይኔ (ምዕራብ አፍሪካ ጊኔ) አገሮች በሙሉ ተገኝተው የማኒ ኮንጎ (ኮንጎ) ንጉሥ ቍጥሩ ከበረከተው ዜጋው ጋር የክርስትናን ጥምቀት ተቀበለ ። ሌሎችም ቀድሞ አረመኔ የነበሩ የዓረብ ፤ የፋርስ የሕንድ አገር ሰዎች በእጃችን ከገቡ በኋላ አንዱ የሌላውን ምሳሌ እየተከተለ ወደ ሃይማኖታችን ገቡ ። ይኸንንም ጉዳይ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በየአገሩ በየሥፍራው የጠፋው መርከባችን ፤ ያለቁት የጦር አለቆችና ፈረሰኞች ከነጭፍሮቻቸው ፤ ያወጣነው የገንዘብ ወጭ ብዙ መሆኑን እያወቅን ይህ ቅዱስ ሥራ ለክርስትና ሃይማኖትና ለግዛታችን መስፋፋት የሚጠቅም መሆኑን በመረዳት ይህ ጉዳይ ወደፊት እንዲቀጥል ከማድረግ በቀር ቻል አላልንም ።

የጦር አለቆቻችንም የኛ ምኞት ምን እንደሆነ በመረዳት ከዚህ ቀደም በሕይወት ያለ ሰው ያልሰማውንና ያላገኘውን አገር እስከ ቀይ ባሕር ወሰን ድረስ በጥንካሬ ዘልቀው ያዙ ። የዚህም አገር ወረዳ ጥንታዊና በቱርኮችና በአረመኔዎች ውስጥ የሚገዛ ነው ። ይኸም አገር የማይደረስበት ነው ለማለት እንኳን ባይቻል እስከ ዛሬ ድረስ ለኛ የተደበቀ ስለሆነ አሁን ሊደረስበት የቻለው በባሕር ላይ መርከባችን በብዙ ማዕበል ከተቸገረና ወታደሮቻችን ብዙ ጦርነት ከአደረጉ በኋላ ነው ። የዚህም ወረዳ (ኤርትራ) ከተገኘ በኋላ ወደ ካህኑ ዮሐንስ (ዓፄ ልብነ ድንግል) ግዛት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ተቻለ ። እርሱና በግዛቱ ያሉት ሁሉ በክርስቶስ የሚያመልኩ ናቸው ። እርሱም ወደኛ ሃይማኖት (ካቶሊካዊት) እንዲገባ አባብለውም ነገሩንም አስረድተውም ተከራክረውም የክርስቲያን መሣፍንት ለሚያከብሩዎና ለሚፈሩዎ በምድር የኢየሱስ ክርስቶስ እንደራሴ ለሆኑት በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር ለተቀመጡት ለቅድስናዎ ታዛዥ እንዲሆን ስል መላክተኞች ላክሁ ። ይኸም ታላቅ ንጉሥ በመልክቶቼ ተደስቶ መላክተኛውን ብዙ ጉዳይ አሲዞ ወደኔ ላከ ። ነገር ግን በዚሁ ጊዜ መካከል ጌታዬና አባቴ (አማኑኤል) ሞቶ እኔ ስለተተካሁ ይኸንኑ ያባቴን ሞት በዚህ አገር አቅራቢያ አገር ለሚያቀኑት የጦር አለቆቹ

እንዲነግሩት አደረግሁ ። ስለካቶሊክ ሃይማኖት ጉዳይ የላክሁበት ተፈጽሞ ማየት ለኔ ታላቅ ደስታ ነው ። እርሱም የላክሁበት ጉዳይ መልካም በመሆኑ ተደስቶ በቶሎ አሁንም በቤተ መንግሥቴ የሚገኘውን መላክተኛውን (ጸጋ ዘአብን) ላከ ብኝ ። ይኸም መላክተኛ የመጣው ቀድሞ ከአባቴና ከጌታዬ (አማኑኤል) ወደዚሁ ንጉሥ (ልብነ ድንግል) ተልኮ ከነበረው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ከሚባለው ቀዳሲያ ችን ጋር ነው ። እነሆ አሁንም ይህ ሰውዬ (አልቫሬጽ) ወደሮማ ለቅድስናዎ አክብ ሮቱን ለማቅረብ ከዚሁ ንጉሥ ተልኳል ። አልቫሬጽንም እስካሁን በዚህ አገር ያቆ የነው የተወደደውን የወንድማችን (ወይስ የእህት) ልጅ አማካሪያችንና መላክተኛ ችንን ፖርቱጋሉን ማርቲኖን ወደሮማ እስክንልከው ድረስ ነው ። አሁን እነሆ በጌ ታው ስም ታዛዥነቱን ሊያቀርብልዎ የመጣውን የዚህኑ የኢትዮጵያን ንጉሥ መላ ክተኛ ጌታውን አልቫሬጽን እንዲያቀርብልዎ ልከነዋል ። ይኸው ንጉሥ ወደኛ የላ ካቸውንም ሁለት ደብዳቤዎች (አንዱ የአማኑኤል መሆኑ ነው ?) እንዲያቀርብልዎ አዘነዋል ። ይህ መላክተኛችን በማናቸውም ረገድ ስለዚህ ጉዳይ የሚነግርዎትን ሁሉ እንዲያምኑትና እንዲቀበሉት እለምንዎታለሁ ። ይኸም ሲሆን በዚህ ታላቅ የቅድስና ቦታ ላስቀመጠዎ ሕያው አምላክ ምሥጋና እናቀርብ ዘንድ ምክንያት ሆኖናል ። ይኸንንም የቅድስና መንበርዎን በሚገባ በጽድቅ በርትዕ በቅድስና ስለ እስተዳደሩት እነሆ አሁን ደግሞ አዲስ ዓለም አዲስ ወደተቀደሰችው የሮማ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ታዛዥዎ የሚሆንISKል ኪዳን ጓደኛ ማግኘታችን ነው ። ይኸም ሲሆን ጠባቂውና አለቃው ለሆኑት ለክርስቲያን አንድነት መስፋፊያ የሚ ሰጠው ጥቅም ወሰን የለውም ። በኔ በኩል ይኸንን ታላቅና ኃያል የሆነ ንጉሥ ከአረ መኔነት (1) ወደ ክርስትና ሃይማኖት (ወደ ካቶሊክ) ልስበው ላስቻለኝ ለእግዚአብ ሔር ምሥጋና እያቀረብሁ በፍጹም ደስብሎኛል ። ይቺም ሃይማኖት ዕድገትና ድል የምታገኘው በዘመናችን ኢትዮጵያን ከአውሮፓ ጋር በቃል ኪዳን ያሠርናት እንደ ሆነ ነው ። እግዚአብሔር ሃይማኖትን እንዲጠብቅ ረዥምና የደስታ ዕድሜም እንዲ ሰጥዎ እለምናለሁ ። በግንቦት ፳፰ኛ ቀን ፲፭፻፴፪ ዓ. ም.» (2) ።

ያፄ ልብነ ድንግልና የዮሐንስ ፫ኛ ጉዳይ የእስላሙን መንግሥት ተርከን ለመ ቃወም በርሱ ጥላ ውስጥ የሚተዳደሩትን ግብፅን ፤ ዓረብን በጦር ኃይል እያስገደዱ ወደ ክርስትና ለመመለስ በማሰብ የሁለቱ አሳብና ምኞት አንድ ነው ። ነገር ግን በዚህ መላላክ ዓፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ ወረራ በፊት ይመኙት የነበረው አንድ ኃይለኛና ሥልጡን የሆነ የክርስቲያን መንግሥት ጓደኛ አግኝተው ከርሱ ጋር ሆነው እስላሞችን ከወጉ በኋላ በወሰናቸው ያለውን አገር እየያዙ እርቶዶክሣዊ ሃይ ማኖታቸውንና ኢትዮጵያዊ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ይሆናል እንጂ ለፖርቱጋል መንግሥትና ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሣሪያ ለመሆን አይደለም ። ይህም የማ

(1) ካቶሊኮች ከኬልቄዶን ጉባዔ ወዲህ የእስክንድርያንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንደ መና ፍቃንና እንደ ውጉዛን ቆጥረው አሁን እረመኔ የሚለው ስለዚህ ይመስላል ። በኛም ወገን አሁን ችግር ቢያቀራርበንም የነሱን ካቶሊካዊ ሃይማኖት ሁልጊዜ እንደሰደብን ነው ።

(2) Dernière partie......ገ. temporal ገጽ 245 - 247

ይከናወን ቢሆን እስከ ዘመናቸው ድረስ የያዙት ሰፊው ግዛታቸው በአዳሎች ዘንድ የበላይነታቸው ከጥንት ተያይዞ እንደመጣው ተፈርቶና ተከብሮ እንዲኖር ነው ።

የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ደግሞ በበኩሉ በሃይማኖት አባቱ በሮማ ሊቀ ጳጳስ ፊት ሊያስመካውና ሊያስመሰግነው የ ሚችለውን አዲስ አገር እየከፈተ በካቶ ሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እያጠመቁ ብዙ ሕዝብ ወደ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስ ቲያን ከማምጣት ጋር ያገሩንም ግዛት ለማስፋት ነው ። በዚሁ ረገድ እስከዚህ ዘመን ድረስ ጳጳሷን ከእስክንድርያ ፓትርያርክ እየተቀበለች በተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንታ የኖረችውን ኢትዮጵያን በሮማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድትተዳደር ለማ ድረግ ነው ። የፖርቱጋል ንጉሥ ከተዋሕዶ ወደ ካቶሊክነት መመለሷን እንጂ የኢ ትዮጵያን የመሬቷንና የፖለቲካ ግዛቷን ለጊዜው የተመኘ አይመስልም ። ስለሃይ ማኖቱ መላከተኞቼን ልኬ ወደኛ ሃይማኖትና በቅድስናዎ ሥልጣን ውስጥ ታዛዥ እንዲሆን እሺ አሰኝቸው እርሱም መላክተኛውን ልኮ ይኸው በቤተ መንግሥቴ ይገኛል ብሏል ። ነገር ግን ያዔ ልብነ ድንግልና የፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ንግግር በጠቅላላው በክርስቲያንነታችን እንተሳሰብ በቃል ኪዳን አንድ እንሁን የተባባሉ ትን መልክተኞቹና ቸልተኛው ጸጋ ዘአብ ግን አስተናጋጆቻቸውን ለማስደሰት እያሉ ኢትዮጵያ ከነንጉሷ ካቶሊክ ሆነዋል ብለው ለንጉሡ ነግረውት ይኸንኑ በፍ ጹም አምኖ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ዓፄ ልብነ ድንግልና ዮሐንስ ፫ኛ በየግላቸውና በየልባቸው ምኞታ ቸው የጉዳያቸው አሳብ ቢለያይም ስለፖለቲካ ያላቸው አስተያየት አንድ ነው ። ሁለቱም ስለ እስላም ውድቀት ፤ ስለክርስትና መስፋፋት ያስባሉ ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ያለፈው አክሱማዊ ገናንነቷ ቀዝቅዞ በዚህ ዘመን ከታናናሽ መንግሥ ታት የምትቆጠር ስትሆን ፖርቱጋል ግን በዓለም የገነነ የጦር ወታደሩ የደረጀ የባ ሕር መርከቦቹ በያለበት እየሄዱ ከታላላቅ መንግሥታት ጋር እየተዋጉ ግዛት የሚ ቀሙ ፤ በዚህም ዘመን እንደሻርል ፭ኛ የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛና የጦር አለ ቆቹ ለክርስቲያን ሁሉ ተስፋና አለኝታ ሆነዋል ። በነአለ እስክንድሮስ ፤ በነአት ናቴዎስ ጊዜ በጠቅላላው በቁስጥንጥንያ መንግሥት ገናና የሊቃውንት መሰብሰ ቢያ የነበረችው የእስክንድርያ ከተማና ቤተ ክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ አገሩን በፊት ዓረቦች ቀጥሎም ግብጾች አሁንም ቱርኮች ስለያዙት በፍጹም እንኳን ባትጠፋ ክብ ሯም ሥልጣኗም ጨርሶ ወድቋል ። ሱልጣኖቹ ፓትርያርኩን እንደፈቃዳቸው እየ ጠሩ ያሥሩ ይፈቱ እንደነበረ ሁሉ ባለፈው ተመልክተናል ።

ስለዚህ ከቀድሞ ዠምሮ በፈረንጆቹ ነገሥታት እየተደገፈ በታላቅነት የኖ ረው የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ግን አሁንም ገናንነቱ ያላቋረጠ የፈረንጆቹ መንግሥታት ሥጋዊ ሥልጣን በተዘረጋበት ሁሉ መንፈሳዊ ሥልጣኑ አብሮ የሚዘረጋ ስለሆነ ዓፄ ልብነ ድንግል ይኸን ሁሉ በማመዛዘን ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ባሕ ርይ ሁለት ባሕርይ እያሉ የሚከራከሩበትን ወደጐን ትተው ላገራቸውና ለመንግሥ ታቸው ደህንነትና ሥልጣኔ ሲሉ የእስላሞቹን እያደር ማየልና ማስጋት በማመዛ

ንና በመፍራት የፖርቱጋሎችን አንዳንድ የሃይማኖት ምኞት በቃል ንግግር ተቀብለው እንደሆነ አይታወቅም ፡፡

አሁን ግን የዚህን ጉዳይ እናቆይና ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ ፡፡ ዶም ማርቲኖ ከዚህ በላይ ከፈረንሳዊኛ ወደ አማርኛ የተረጐምነውን የንጉሡን ደብዳቤ ለሊቀ ጳጳሱ አቅርቦ ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ በርሱው አማካይነት የኢትዮጵያ ንጉሥ ያዔ ልብነ ድንግል መልክተኛ ተብሎ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በተራው ቀረበ ፡፡ የዣን ቴምፖራል መጽሐፍ በዘመኑ ከጉባዔ ጸሐፊ ላይ ቀድቶ እንደሚለው አልቫሬጽ የሊቀ ጳጳሱን መዠመሪያ እግሩን ከዚያ እጁን ቀጥሎ ጉንጩን ስሞ ከኢትዮጵያ ንጉሥ የተላከውን የወርቅ መስቀልና ደብዳቤ አቀረበ (1) ፡፡ ምናልባት እንደዚህ ያለውን አሳሳም አልቫሬጽ ያደረገው ዓፄ ልብነ ድንግል አዘውት በርሳቸው ስም ይሆናል ፡፡

የመስቀሉ ወርቅ ሚዛኑ አንድ ሊቨር (ግማሽ ኪሎ ?) መሆኑን ደብዳቤውም መዠመሪያ ከኢትዮጵያ ቋንቋ ወደ ፖርቱጋል ተተርጉሞ የነበረውን አሁን ደግሞ ወደ ላቲንና ወደ ኢጣልያ ቋንቋ ተተርጉሞ በሊቀ ጳጳሱ ዋና ጸሐፊ ተነቦ ሊቀ ጳጳሱ እንደሰሙት የዣን ቴምፖራል ጽሑፍ ይገልጽልናል (2) ፡፡

ዓፄ ልብነ ድንግል ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ የላኩት ደብዳቤ ለፖርቱጋል ንጉሥ ከላኩዋቸው ደብዳቤዎች ፲፭፻፳፩ ያህል ልዩነት የለውም ፡፡ ደብዳቤዎቹ ሁለት ናቸው አንደኛውን የመጨረሻውን አንባቢ ይመለከታቸው ዘንድ ከትርጉም ወደ ትርጉም ሲዘዋወር ከወረደበት ከቀድሞው ፈረንሳዊኛ ላይ ከዚህ እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ ፡፡

«የሚታየውንና የማይታየውን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ፤ ከአምላክ እውነተኛ አምላክ ከብርሃናት እውነተኛ ብርሃን በሆነ ከጥንት ዠምሮ ከአብ ጋር አንድ በሆነ በእግዚአብሔር ወልድ ፤ ከአብ በሠረፀ በሕያው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ስም ፡፡ እኔ በእግዚአብሔር ጸጋ የነገሥሁ ፤ አንበሳ (ወናግ) ሰገድ ተብዬ የተሠየምሁ ፤ ነገር ግን ደንበኛው ስሜ እጣነ (ልብነ) ድንግል ይኸውም ማለት ድንግል ያበራችለት ፤ የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ልጅ የበእደ ማርያም የናሁ (ናዖድ) ልጅ በሥጋ ፤ የቅዱስ ጴጥሮስና የቅዱስ ጳውሎስም ልጅ ፡፡ ትልቁ ጌታ ቅዱስ አባት ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን ፡፡ ኃያሉና ቅዱሱ ፤ የዓለም ጳጳሳት አለቃ ፤ ሁሉ የሚፈራህ ፤ ሕያው የሆነ ሁሉ ባንተ ላይ ሊራገም የማይገባው ፤ የነፍሳት ገዥ ፤ የብፅአተኞች ወዳጅ ፤ የሃይማኖት ሰባኪና ጌታ ፤ ሕሊናንና እውነትን የሚቃወሙ ነገሮች ጠላት መልካም ሥርዓትንና ልማድን አፍቃሪ ፤ ቅዱስ የተባረክኸው ከሁሉ በሁሉም ላይ የተመሰገንኸው ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ሥልጣንና ክብርን ላገኘኸው ላንተ የሁሉ አባት ለሆንኸው ለቅዱስ አባት ከሌሎች ጳጳሳት የበለጠ ቅዱሳን ሐዋርያት (፫፻፲፰ ሊቃውንት ?) እንዳዘዙት አክብሬ ታዛ

(1) ዣን ቴምፖራል . . . . . ገጽ 257 - 262
(2) ዣን ቴምፖራል . . . . ገጽ 263

ኸሆ እሆናለሁ ። እንደ ንጉሥም ፈርቼ አከብርሃለሁ . . . . . . በቅዱስ ጴጥሮስ ፈንታ (የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ ነህ ብዬ) አክብሬ እሰግድልሃለሁ እኔ እንደጌታዬና እንደ አባቴ እንደምመለከትህ አንተም እንደልጅህ እንድትመለከተኝ ከልቤ እለምንሃለሁ ። ከሮማ የመጡት በነገሩኝ ብቻ መንበረ ጵጵስናህን በአክብሮት እመለከታለሁ . . . . . . ከሁሉ ቦታ ከኢየሩሳሌምም መንበረ ጵጵስናህንና የቅዱሳኑን የሐዋርያትን በር ለመጐብኘት ይመጣሉ ፤ ክርስቲያን በመሆናቸውም በጉዟቸው ሁሉ ችግር አይገጥማቸውም . . . . . . እንደ መልአክ የምቆጥረውን መልክህን ለማየት . . . . . . ቅዱሳን ንግግሮችህን ለመስማት . . . . . . . እመኝ ነበር ። ነገር ግን ለጊዜው አልሆነልኝምና እስከዚያ ድረስ መልእክትህንና ቡራኬህን እየላክህ እንድታጽናናኝና በክርስትና ሃይማኖት እንድታጸድቀኝ እለምንሃለሁ ። የጠባቂነት (እረኝነት) ቀለበትህን ስታደርግ የኔን የወዳጅነት አክብሮት እንድታስብ ። እነዚህንም በደብዳቤ የምልክልህን ጥዑመ ቃሎች እንድትዘክር እለምንሃለሁ ። በዚህም ላይ ሰላም ሲጨመርበት የሰው ልጅ ደስታው የተጠማ ሰው በቀዝቃዛ ውኃ እንደሚረካ ፤ ሙሉ ይሆናል ። እኔም በዚሁ ረገድ ከኔ አገር ርቆ የሚገኘውን ያንተን ቅድስና የሚመለከተውን ጉዳይና የክርስቲያኖቹን መሣፍንት ወሬ መስማት ደስታ ይሰጠኛል ። ዛሬም በቀላል መላላክ የተቻለው የፖርቱጋል ንጉሥ በርኅራኄው መንገዱን ስለከ[illegible]መልክተኞቹን ገና አባቱ (አማኑኤል) በሕይወት ሳለ ልኮብኝ ስለነበረ እኔም ከዚያ ወዲህ ከማንም ከክርስቲያን ንጉሥም መስፍንም ጳጳስም መልክተኛም ደብዳቤም አልተቀበልሁም ። አንድ ብቻ ደብዳቤ ቀድሞ ከኤውዥን ጳጳስ (ወደ ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ) መጥቶ ነበር ። ከብዙው ንግግሩም ውስጥ አንዳንዱ ልጁ ዣን ፖሌዎሎግ የሮማውያንና የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ከመሞቱ በፊት ወደ ቅዱስ ጉባኤ የቁስጥንጥንያን ፓትርያርክ ብዙ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት አስከትሎ እንደመጣ ከመጡትም ውስጥ የአንጾኪያ ፤ የእስክንድርያ ፤ የኢየሩሳሌም ፓትርያርክ መላክተኞቹ ተጨምረው መጥተው ቀድሞ በጥርጣሬና በወንጌል አሳብ ልዩነትና ክርክር የነበረው ቀርቶ ዛሬ በክርስትና ሃይማኖት ፍጹም ስምምነት አድርገው ጳጳሱም በጉባዔው የነበሩትን ሁሉ እንደወደዳቸውና እንዳከበራቸው ይገልጻል ።

አሁን ግን እላይ የተጠቀሰው ሊቀ ጳጳስ ኤውዥን ልኮት የነበረውንና እስካሁን ድረስ አክብረን ያቆየነውን መጽሐፍ በውስጡ ያልታረመ ነገር ስላለበት መልሼ ይኸው ልኬዋለሁ ። ከዚሁም ጋር ስለሊቀ ጳጳሱ ቡራኬና ኃይል የሚናገረውን ልኬያለሁ ። መጽሐፉም ከባድ የሆነው የጳውሎስ መልእክት (ለአሕዛብ) ስለተጨመረበት ነው ። ይኸንንም መጽሐፍ በፊት ከኤውዥን ዘንድ ተልከው ወደኛ ያመጡት የክርስቶስ አገልጋይ የሆኑት ቴዎዶር ፤ ፒዬር ፤ ዲዲም ፤ ጕርዥ (ቴዎድሮስ ፤ ጴጥሮስ ፤ ዲድምያኖስ ፤ ጊዮርጊስ) ይባላሉ ። የዚህንም የመልክትና የመጽሐፍ ጉዳይ መዝገብዎን (አርሽብዎን) ቢያስመረምሩት ነገሩ ሊከበር የሚገባ ለልጅ ልጅ ሊተላለፍ የሚችል ዋና ገንዘብ መሆኑን ሊገነዘቡት ይችላሉ ። እኔም ደስ የሚያሰኝዎትንና የሚያዙኝን ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ ። ይኸንንም የማደርገው ሮም ሆነው በዓለም ላይ ለመፍረድ በተመደቡት በቅዱሳን ጴጥሮስና ጳውሎስ

ከተማ ላይ ለመታሰቢያ የሚሆን ነገር፣ትቶ የሚሞት ሰው ሕያውና ደስተኛ መሆኑን ስለማውቅ የአምላክዎን ጸጋ የሊቃውንቱንም ጉባዔ ሞገስ ለማግኘት ስል ያሁኖቹን ደብዳቤዎች ላክሁብዎ ። ከዚህም ጋር ተስፋ የማደርገው ቡራኬዎን እንዲልኩልኝ ነው ። ቀጥሎም ሥዕሎች ይልቁንም የቅድስት ድንግል ማርያምን ቢልኩልኝ ከትልቅ ስጦታ ቆጥሬ አምላካዊ አሳብዎ (ውለታዎ) በልቤ ተቀርጾ ይኖራል ። ከዚህም በተረፈ የመጻሕፍት ሊቃውንትና መምህራን ሥዕልም ሰይፍም አናጢም ገንቢም ፣ እጡብና ድንጋይ ጠራቢዎች ፤ መለከት እምቢልታና ይኸን የመሳሰለውን ሁሉ የሚሠሩ ሙዚቀኞች ይላኩልኝ ። እኔም እንዚህ ሁሉ ቢመጡ በመልካም ይገሮ ዋጋቸውን ሳላስቀር በትርፍ የምሰጣቸውንም አንዳንድ ነገር ሳልቆጥር ወደ አገራችንም መመለስ ደስ ይለናል ባሉ ጊዜ ሳላውክ በነፃነት ለቅቄ እንደምሰዳቸው አሁን የምሰጠው ተስፋ የተረጋገጠ ነው ። ማንንም ቢሆን በግድ ባገሬ ላይ ማስቀረት አልወድም ። ቅዱሱ አባት ሆይ በጕረቤትዎ ያሉት (ፖርቱጋል ፤ ፈረንሳዊ ፣ ጀርመን ፤ ኤስፓኝ) ልጆችዎ የክርስቲያን ነገሥታት ባንድነት ተስማምተው በአሕዛቦቹ በመሐመድ ተከታዮች ላይ ትልቅ ያለም ጦርነት ለማድረግ የሚነሡት መቼ ነው ? ። አለመስማማታቸውስ በምን ምክንያት ነው ? ብዬ ልጠይቅዎት እወዳለሁ ። እኛ ክርስቲያኖቹ ባንድነት ብናብር ኖሮ በመዲና የሚገኘውን የመሐመድን መስጊድ ማፍረስ እንችል ነበር ።

ISIC

ስለዚህ እነዚህ የክርስቲያን መንግሥታት እንዲስማሙ እንዲያዟቸው እርስዎም የዚህን ነገር አስበውበት የክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ እርዳታዎንና አዳኝነትዎን እንዲፈጽሙ እለምንዎታለሁ ። የኔ የመንግሥቴ ወሰን በመሐመዳውያን እርስ በርሳቸው በሚደጋገፉት እስላሞች የተከበበ ነው ። እነሱ ይኸን ሲያደርጉ (ሲደጋገፉ) እኛስ የክርስቲያን መሣፍንትና አለቆች የሆንነው ባንድነት ልንደጋገፍ የሚገባን ጊዜው አሁን አይደለምን ፤

በወሰኔ ላይ አንድ የእስላም ንጉሥ አለ ። እርሱም የኔን ጦር መመከት ስለአቃተው ከሕንድ ፣ ከፋርስ ፣ ከዓረብ ፤ ከግብጽ ነገሥታት ጋር ቃል ኪዳን እያደረገ ከነርሱ በሚያገኘው እርዳታ እኔን ያላንዷች ክርስቲያን ንጉሥ እርዳታ ብቻዬን ያለሁትን እየወጋ በጣም የሚያናድድ ታላላቅ ጦርነት አድርጎብኛል (1) ። ይኸንንም ሁሉ የምነግርዎ መሣሪያ እንዲላክና አሳቤ እንዲፈጸም ብቻ ሳይሆን እነዚህን ..... ከወሰኔ ለመግፋት በማደርገው ጦርነት በጸሎትዎ እንዲያስቡኝ ለእግዚአብሔርም አደራ እንዲሉኝ ። እነዚህንም ተንኮለኞች . . . . . የምዋጋበት መሣሪያ የሚሠሩ ልኝን እላይ የጠቀስሁዋቸውን ሰዎች እንዲልኩልኝ እርስዎና ወንድሞቼ የክርስቲያኑ ነገሥታት እርዳታቸውን እንዲያደርጉልኝ ነው ። ከነርሱም ጋር በጸናችው የክርስትና አንድነት ስለተሣሠርን ይኸንን እርዳታ ሊልኩልን አግባብ ነው ። ስለዚህም ስለልጁ ስለክርስቶስ ክብር ቀናውን አሳብዎን ይፈጽምልዎት ዘንድ እግዚአ

(1) በመዠመሪያ ጊዜ በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ከማኅፉዝ ጋር ያደረጉትን ይሁን ወይም በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ላይ የተደረገውን የግራኝንና የፋኑኤልን ጦርነት መጥቀሳቸው ይሁን ተለይቶ አይታወቅም ።

ብሔርን እለምናለሁ ። ያሁኑን ደብዳቤና ገጸ በረከት በኃያሉና በትልቁ አማኑኤል ልጅ በዶም ዮሐንስ አማካይነት ታማኙና የተወደደው መላክተኛችን ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ እንዲያቀርብልዎት ልኬዋለሁ» (1) ።

የደብዳቤው ቃል ይነስ ይብዛ ከዚህ በላይ የተገለጸው ነው ። ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ይኸን ደብዳቤ ባቀረበበት ቀን ስለሆነው ሁኔታ የዣን ቴምፖራል መጽሐፍ በመጠኑ እንደዚህ ሲል ይገልጽልናል ። ጌታው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ደብዳቤውን ባቀረበ ጊዜ በራሱ ቋንቋ በፖርቱጋል የተናገረውን የፖርቱጋል ንጉሥ መላክተኛ (የዶም ማርቲኖ) ጸሐፊ በጉባዔ የተቀመጠው ሁሉ ይሰማ ዘንድ በላቲን ቋንቋ ተረጐመው ። ቃሉም ይህ ነው ፤ "ጌታውና የታደልኸው አባት ሆይ የላይኛውና የታችኛው ኢትዮጵያ ንጉሥ ካህኑ ዮሐንስ የምንለው ኃያሉና ክፍ ያለው ዳዊት (ዓፄ ልብነ ድንግል) የክርስቲያን ሁሉ አለቃ የጴጥሮስ ተከታይ የክርስቶስ እንደራሴ ለሆኑት ለቅዱስነዎ ያለውን ታዛዥነቱን በስሙ እገልጽልዎ ዘንድ ላከኝ ። ይቺንም ትንሽ የወርቅ መስቀል እንደ ገጸ በረከት የላከልዎትን በደስታ እንዲቀበሉዎት እምኛለሁ ። ለዚህም ገጸ በረከት ግምት የሚሰጡት ትንሽ ለሆነው ለዋጋው አይደለም ። ነገር ግን ክርስቲያን ሁሉ ደኅንነት ያገኝ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምንና ሞትን የተሸከመበት የተከበረ መስቀል በመሆኑ ነው ። እንደዚሁም ታዛዥ ልጅ ላባቱ እንደሚያቀርበው ገጸ በረከት አድርገው ይቀጠሩት ።»

አልቫሬጽ ከዚህ በላይ ለተናገረው ቃል በሊቀ ጳጳሱ ልዩ ትእዛዝ የሊቀ ጳጳሱ ጸሐፊ ከዚህ የሚቀጥለውን መልስ ሰጠ ።

«በጣም የተቀደሰው አባታችን ሊቀ ጳጳሱ በቅን ልብ በአባትነት ፍቅር ደስ በተሰኘ ልብ በጣም ኃያል የሆነውን የኢትዮጵያን ንጉሥ የዳዊትን መልክተኛ ዶም ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን ከታዛዥነት ከገጸ በረከቱና ከደብዳቤው ጋር ተቀበለው ። በሩቅ አገር ካለው በጣም ክርስቲያን ከሆነ የውጭ አገር ንጉሥ የተከበሩ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ወንድሞች ካርዲናሎች በተሰበሰቡበት ጉባዔ መላክተኛውን ልኮ የታዛዥነቱን ቃል በዘመኑ ስለአሰማው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ ። ስለዋጋውም ብቻ ሳይሆን ስለላኪው ፍቅር ሲል ገጸ በረከቱን መስቀሉን በደስታ ተቀብሎ ያዘው ። የፖርቱጋል ንጉሥ ከላይኛውና ከታችኛው ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዳዊት ጋር የቃል ኪዳን ዝምድና በማድረጉ ጌታችንን አመሰገነ ።

በቀረፈ የቀረው ከኢትዮጵያ ንጉሥ የቀረበለት ጉዳይ እንደ አገሩ ርቀት የተቻለው ሁሉ እየታየ እንዲፈጸም ቅዱስ አባት አዘዘ ። በአጠገቡ ላሉት ለሚወዱትና ለሚያከብሩት የክርስቲያን መሣፍንት እንደሚያደርገው ያባትነት ፍቅር የኢትዮጵያንም ንጉሥ በአጠገቡ እንዳለ እንደልጁና እንደወዳጁ ሊቆጥረው ወሰነ ። የኢትዮጵያ ንጉሥ ስለላካቸው ደብዳቤዎችም ጉዳዩ አንድ ባንድ እየታየ ካንተ (ከአልቫሬጽ)ና ከፖርቱጋል ንጉሥ መላክተኛ (ዶም ማርቲኖ) ጋር እየተስማማን መልስ ይሰጣል አለ ። ይኸም ቃል ከተነገረ በኋላ ጉባዔው ተፈታና ሁሉም ወደየጉዳዩ ተበተኑ ።»

(1) Jean Temporal............. ገጽ 259 - 260

ይህ ያዒ ልብነ ድንግል ደብዳቤ የሮማን ሊቀ ጳጳስ እንደአባት ቆጥሮ ታዛዥነ
ትንና ልጅነትን ይጠይቃል ። በንግግሩ ውስጥ ያለውን ሁሉ እንባቢ ስለተመለከ
ተው አሁን እኔ እንድደግመው አያስፈልግም ። ይኸን ሁሉ ዝምድናና ቃል ኪዳን
የቤተ ክርስቲያናቸውና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ባላንጣ ከሆነው ከሮማ
ሊቀ ጳጳስ ጋር ለማድረግ የፈለጉበት ምክንያት ባላገሮቻቸውን የአዳልን ሱልጣኖች
እየደገፉ የሚያስወጉዋቸውን የግብጽን የዓረብን መንግሥታት ለመቃወም ሲሉ
ነው ። ይኸን በጻፉበት ጊዜ በእርግጥ ወደፊት ግራኝ የሚያደርገው ወረራ ተሰምቷ
ቸው ነበር ለማለት ይቻላል ። ንጉሡ በደብዳቤያቸው እንደገለጹት የሐረር ሱልጣን
ከዓረብ ፣ ከሕንድ ፣ ከፋርስ ፣ ከግብጽ በየጊዜው እርዳታ እያገኘ ሲወጋቸው እርሳቸው
ያላንዳች ክርስቲያን መንግሥት ድጋፍ ብቻቸውን በእስላሞች ተከበው መቀመጣ
ቸው አሳዝኗቸው ለወደፊቱም ይህ ሁኔታ የማይዘለቅ መሆኑን ስለገመቱ ከፖርቱ
ጋል ንጉሥ ጋር ቃል ኪዳንና ጥብቅ ወዳጅነት ፈለጉ ። የዚህ ጉዳይ ደግሞ የሮማ
ሊቀ ጳጳስ ካልገባበት ፍጻሜ ለማግኘት አይችልም ብለው በአጠገባቸው ያሉት
ፖርቱጊዞች ይጋግመው ስለመከሩዋቸው ከዚህ በላይ በጻፉት ዓይነት የሮማን ሊቀ
ጳጳስ ዝምድና ለመፈለግ ተገደዱ ። አልቫሬጽ በመጽሐፉ ምዕራፍ ፳፮ ላይ
እንደገለጸው ይብዳቤው ራሱ የተዘጋጀው በአልቫሬጽና በነኮቪልሐእ ምክርና
አሳብ ስለሆነ ሊቀ ጳጳሱን ሊያስደስተው የሚችል ብዙ የአክብሮት ቃል እንደሞላ
በት ይታያል ።

ISIC

የተዋሕዶ ሃይማኖታቸው መሪ እንዳባታቸው የሚያዩት የእስክንድርያው
ሊቀ ጳጳስ በዚህ ጊዜ በግብጾቹና በቱርኮቹ ሱልጣኖች ውስጥ ወድቆ ክቡሩም ገና
ንነቱም የጠፋ ያህል ስለሆነ ንጉሡ የሮማውን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት መለማመጥም
ማክበርም ግዴታቸው ሆኗል ማለት ነው ። የቀለም ፤ የዕውቀት መደብር የሊቃው
ንት መሰብሰቢያ የነበረችው ገናናዪቱ እስክንድርያ የእስላሞች ሥልጣን ስለወረ
ራት ምንም እንኳን ይኸን ደብዳቤ በጻፉበት ዓመት (፲፭፻፲፯ ዓ.ም.) በአጠገባቸው
ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ ቢኖሩም በጣም አርጅተው ራሳቸውም የሚሰጡት
አባታዊ ምክርም ስለተዳከመ ከዚች ከእስክንድርያ ከተማና ከፓትርያርኳ እርዳ
ታና አለኝታ ከቀረ ብዙ ጊዜ መሆኑን ንጉሡ ተገንዝበውታል ። ስለዚህ ከዚህ በላይ
ያለውን ለሮማ ሊቀ ጳጳስ የሚያስደስተውን ንግግር አልቫሬጽና ክርሳቸውም ወገን
ባለፈው ዓባይ ዳር በተደረገው ጦርነት ተይዞ በአብሳማ ኑር እጅ የተገደለው ዓቃቤ
ሰዓት ነገደ ኢየሱስና ሊቁ አቡሂር በምክር አዘጋጅተው ያቀረቡላቸውን ደብዳቤ
ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ላኩ ። በደብዳቤው ቅዱስ አባት ፣ የጴጥሮስ ተከታይ ፣ የኢየ
ሱስ ክርስቶስ እንደራሴ በማለታቸው ፤ የነፍሳት ገዥ የሚልና ይኸን የመሳሰለ የአ
ክብሮት የአድናቆት የማግነን ቃል በመጨመራቸው የካቶሊክ ሃይማኖትን የሚያ
ምኑትን ሰዎች ደስ ይላቸው እንደሆነ ተዋሕዶዎቹ ደግሞ በዚህ ይዞታ ያዝኑ እንደ
ሆነ አይታወቅም ። ነገር ግን ደብዳቤውን ያዘጋጁት እነማን መሆናቸው ሲታወቅ
ደብዳቤው የተጻፈበት የችግር ወቅት ሲመዛዘን ማንንም ሊያሳዝን ማንንም ሊያስ
መካ አይችልም ።

በቀድሞ አጻጻፍ ውስጥ ይኸን ቃል ብጨምር እንደዚሀ ያለውን ትርጉም አምጥቶ በሕግ ያሲዘኛል የሚባል ጥብቅ ጥርጣሬና የንግግር ቁጠባና ወሰን በዚያን ዘመን ስለሌለ ዓዔ ልብነ ድንግልም ሌሎቹም ነገሥታትና መሣፍንት መኳንንትና ጳጳሳት ሁሉ እርስ በርስ ሲጻጻፉ ቃለ አጋኖ በአክብሮት ላይ አክብሮት በመጨመር የሚጽፉለትን ባለሥልጣን በተቻለ ማስደሰት ልማድ ነበር ። እንኳን በዚያ በሩቁ ዘመን አሁንም ባንዳንድ ክፍል አንዱ ለሌላው ባገራችን ደብዳቤ ሲጽፍ "ኀበ ክቡር ወልዑል መፍቀሬ እግዚአብሔር ወሰብእ" ሲለው በእርግጥ የሚጻፍለት ሰውዬ ክቡርም ልዑልም ያልሆነ ወይም ያልተባለ የእግዚአብሔርና የሰው ወዳጅ ከፍ ያለና የከበረ መሆኑንም አመዛዝኖ አይደለም ። ነገር ግን ይኸን የሌለውን ማዕርግና ቅጽል እጥግቦ በመስጠት ጸሐፊው የሚፈልገውን ጉዳይ ለማከናወን ነው ።

የሆነ ሆኖ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ይኸን ደብዳቤና ገጸ በረከት ለሊቀ ጳጳሱ በአቀረበበት ጊዜ ፲፭፻፴፫ (እንደ ኢት. ቀ. ፲፭፻፳፭ ዓ. ም.) ግራኝ አህመድ ባለፉት ሁሉ ምዕራፎች እንደተመለከትነው የደቡብን ኢትዮጵያ በሙሉ ይዞ ከዚያ አልፎ ወደ ሰሜን ሄዶ ከትግሬ ወደቤገምድር ንጉሡን እግር በግር እየተከታተለ የተረፈ ጦራቸውን እየወጋ እርሳቸውንም ለመማረክ የሚጥርበት ጊዜ ነው ። አልቫሬጽ ከጸጋ ዘአብ ጋር ይኸን መልእክት ለማድረስ ከኢትዮጵያ በ፲፭፻፳፮ (፲፭፻፲፰ ዓ. ም.) የሄደ ጊዜ በ፡ሀ፡፡ን ከመዋጋት በቀር ግራኝ የኢትዮጵያን ግዛት ገና አልወረረም ነገር ግን ወዲያው ባመቱ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ግራኝ በደዋሮ ራስ ደገልሃንን ወግቶ እንዳሸነፈ ይታወሳል ። ዋናው ውጊያውም የተዠመረው ያን ጊዜ ነው ማለት ይቻላል ።

አልቫሬጽ ይኸን ደብዳቤ ለጳጳሱ ያቀረበው በሄደ በሰባት ዓመቱ ነው ። ከዚህ በፊት እንዳልነው ባሁኑ ሰዓት ግራኝ አህመድ ያደረገውን ወረራ የአብያተ ክርስቲያናቱን ቃጠሎ የታላላቆቹን መኳንንት እልቂት የንጉሡን በያለበት መሸሽ ከአገሩ ርቀት የተነሣ በፍጹም አልሰማውም ይሆናል ። ቢሰማ ኖሮ ጉዳዩን ለጳጳሱ ሊጠቅስ በቻለ ነበር ። በእርግጥ የዚያን ዘመን ግንኙነት በጣም አስቸጋሪ ስለ ነበረ መንገዱንና መተላለፊያውንም የቱርክና የግብጽ ኬለኞች ስለሚዘጉት ክርስቲያንም ከአፍሪካ ወደ ፈረንጅ አገር ማለፍ ችግር ስለሆነ አልቫሬጽም የሮማ ጳጳስም የፖርቱጋል ንጉሥም ግራኝ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገውን ወረራ አልሰሙም ለማለት ይቻላል ። ያለዚያ ስለ ንጉሡና ስለጣሉበት አደራ እንኳ ባይተጋ እላይ እንዳልነው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ በንጉሡ ዘንድ ስለአገኘው ክብር ስለሹመቱም ስለ ክርስትና ቅናትም ሲል እንደምንም ወትውቶ በቶሎ የጦር እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ይዞ ሳይመጣ አይቀርም ነበር ።

በዚህም ላይ የፖርቱጋሎቹ መልክተኞች ከኢትዮጵያ በሄዱ ባመቱ ጦርነቱን የዠመረው ግራኝ አህመድ የቱርኮቹንም እርዳታ ሊያገኝ የቻለው ዋናው በዚሁ በተወጠነው በኢትዮጵያና በፖርቱጋል ወዳጅነት ምክንያት መሆኑን ስለ ማይስቱት የሰዉን እልቂት የአብያተ ክርስቲያናቱን ፣ የገዳማቱን መበዝበዝና

መቃጠል በትክክል ሰምተው ቢሆን ኖሮ የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማ ሊቀ ጳጳስ ይኸን ያህል ችላ ሊሉ አይችሉም ነበር ።

## ምዕራፍ ፹፰

## ባዬ ልብነ ድንግል ዙሪያ ያሉት ፈረንጆች - ከመካከላቸው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ወደ ሮምና ወደሊስቦን እንደተላከ ። (፲፭፻፳፯ ዓ. ም.)

ሰውና ወርቅ በኔ ዘንድ እንደ ባሕር አሸዋ ወይንም እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተ ነው ብለው ዓፄ ልብነ ድንግል በሰላሙ ጊዜ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ ፫ኛ እንደ ጻፉት ይኸን የበረከተ ወርቅና ሕዝብ በደንብ ይዞ የሚጠቀምበት ካለመኖሩ የተነሣ እነሆ ሕዝቡም የደፈረው እየተዋጋ ያልቃል ፤ አንገቱን ለሠይፍ አሳልፎ መስጠት የሰቀጠጠው ወደ ግራኝ እየገባ ሰልሞ የሚመጣውን ጊዜ ይጠብቃል ። ለግራኝም ሳይገባ ተዋግቶም ሳይሞት በሕይወት ከንጉሡ ጋር ወይም ለብቻው በአ ውራጃው ሆኖ ከግራኝ ጦር ጋር ከፍ ባለ ተጋድሎ ውጊያውን የሚቀጥለው በያለ በት ሞልቷል ። እንኳን ባልተያዘው አገር በተያዘው በደቡብም ክፍል ሕዝቡ አልፎ አልፎ ሁል ጊዜ የግራኝን ጦር ከመቃወም አላረፈም ። ይኸውም የኢጣልያ ጦር በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. አገሪቱን የወረረ ጊዜ አርበኞች በያለበት ተበታትነው ከተከ ላከሉት ጋር የሚመሳሰል ነው ።

በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ቁጥራቸው እንደ ዓረብ ፋቂህ አጻጻፍ አርባ የሚደርስ የውጭ አገር ሰዎች በዚህ በመከራና በጦርነት ሰዓት ካፄ ልብነ ድንግል ጋር አሉ ። አንዳንዶቹንም እንደ አው ቍጥር ፲፭፻፳ ዓ ም ከጓደኞቹ ጋር መጥቶ ፮ ዓመታት ቆይቶ ወዳገሩ የተመለሰው አልቫሬጽ በፊተኛው ጊዜ አግ ኝቶ አነጋግሯቸዋል ። ከነርሱ ውስጥ ኢትዮጵያና ንጉሷን ፈልጋችሁ አግኙ ተብ ለው ከፖርቱጋል ንጉሥ ከዮሐንስ ፪ኛ ታዘው ከመጡ በኋላ አንደኛው ፖይቫ የሚ ባለው በርበራ ሞቶ ፪ኛው ፔድሮ ደ ኮቪላሃን የሚባለው ነው ። ይኸም ሰው ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ባፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፸ - ፲፬፻፹፮) ነው ። እርሱም እነ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ የመጡ ጊዜ አግኝተውት ዋና አስተርጓሚ ሆኖ እንዳገለገላቸውና የእስላሞቹንም የክርስቲያኖቹንም ቋንቋ (ዓረብኛና አማርኛ) አጣርቶ እንደሚያውቅ ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ደብዳቤ በጻፉበት ጊዜ ከሊቃውንቱና ከነአልቫሬጽ ጋር በሥራውም በማስተርጐምም አብሮ እንደ ሠራ ያነበብነው ትዝ ይለናል (1) ።

እንደዚሁም ባፄ በእደ ማርያም ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፷ - ፲፬፻፸) የነበረ ውና በንጉሡ ትእዛዝ የአትሮንስ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን በሥዕል ያስጌጠው

(1) አልቫሬጽ ምዕ. 104

ብራንካ ሌዎን የሚባለው የቬኔዚያ ተወላጅ አልቫሬጽ አግኝቶት ሥዕሉንም ጐብኝቷል ። ሕዝቡም መርቆርዮስ እያለ ይጠራው ነበር ፤ እኛ በምንቀድስበት ጊዜ የኛን የቅዳሴ የቃሉን ፍች ላበሾቹ ይተረጉምላቸው ነበረ ሲል ገልጿል (1) ። ነገር ግን ከበእደ ማርያም ጀምሮ እስከዚህ እስከ ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ድረስ ከ፶ ዓመት የበለጠ ጊዜ ስላለፈ በአሁኑ የጦርነት ሰዓት ይኑር ይሙት አይታወቅም ።

ሙሴ ሬኔ ባሴት የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊኛ በተረጐሙት ላይ በዚያ ዘመን ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ስለነበሩት የውጭ አገር ሰዎች መግለጫ ሲሰጡ እንደዚህ ብለዋል «በ፲፭፻፲፯ ዓ.ም. ሎፖ-ሱአሬዝ የሚባለው የፖርቱጋል የጦር መኰንን በመርከብ መጥቶ የጅዳህን ወደብ የደበደበ ጊዜ በዓረቦች እጅ ታስረው የተቀመጡትን አበሾችንና ፈረንጆች ነፃ አውጥቷቸው ከነዚሁ ፲፯ የሚሆኑት ወደ ዓፄ ልብነ ድንግል ተልከው መጥተዋል ። ከነርሱ መካከል ሁለቱ የካታላን (ኤስፓኝ) አንዱ ግሪክ (ደቢሆ) አንዱ የባስክ (ደቡብ ፈረንሳዊ) አንዱ የጀርመን የቀሩት የጀኖቫ (ኢጣልያ) ተወላጆች ናቸው» (2) ።

አልቫሬጽ በበኩሉ በመጽሐፉ ምዕ. ፩፻፳ ላይ ንጉሡ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል የሐድያ ግዛታቸውን ሲጐበኙ በሄዱ ጊዜ ፳ ወይም ፲ ጀኖቫውያን ነበሩ ይላል።

በነዚህ ላይ ደግሞ በዚህ መጽሐፍ በመጀመሪያው ክፍል እንደተመለከትነው ዓፄ ልብነ ድንግል እንደ አው. ቍ. በ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. የመጡትን ፖርቱጋሎች በ፲፭፻፴፮ ዓ. ም. መልሰው ጸጋ ዘአብን ጨምረው ሲልኩ ከመካከላቸው ሐኪሙ ዮሐንስ(Phisico Mestere Joao) የሚባለውን ሐኪምና (3) ። አልአዛር የእንድርያሱ (Lazardo Di Andrade) የሚባለውን ሠዓሊ ሁለቱን አስቀርተዋል ።

እነዚህ ሁሉ የውጭ አገር ተወላጆች በዚህ በጦርና በመከራ ሰዓት ከንጉሡ ጋር አብረው ከመንዝ መከራውንና ችግሩን ከመካፈል በቀር አብዛኞቹም ያረጁ አንዳንዶቹም የሃይማኖት ሰዎች ስለሆኑ በምንም ዓይነት ውጊያ ሊረዱ የቻሉ አይመስልም ። ቢበዛ የጦር መላና አንዳንድ የሚታያቸውን ምክር ያቀርቡ እንደሆነ ነው እንጂ ሰይፍና ጦር ጨብጠው ከተዋጊው ወታደር ጐን ተሰልፈው መዋጋታቸውን ዓረብ ፋቂህ አንድም ቦታ አያወሳም ። ታሪክ ነገሥትማ የፖርቱጋሎቹን መምጣታቸውንም መሄዳቸውንም የነዚህንም አርባ የውጭ አገር ሰዎች መኖራቸውን አያወሳም ።

ስለዚህ ባለፈው ምዕራፍ እንደተገነዘብነው ከኢትዮጵያ የንጉሡን ደብዳቤና ገጸ በረከት ይዘው ወደ ሊስቦን የሄዱት አልቫሬጽና አባ ጸጋ ዘአብ ፮ ዓመት ሙሉ የተላኩበትን ጉዳይ ፈጽመው መልስ ሳያመጡ ስለቀሩና ድምጻቸው ስለጠፋ የሮማ ሊቀ ጳጳስና የፖርቱጋሉም ንጉሥ ምንም እንኳን ባለፈው እንደተነበበው የኢትዮጵያን ፍላጐት ቢረዱት በዚያው በአውሮፓ በየራሳቸው ጉዳይ ተጠምደው የኢትዮጵያን ጉዳይ ችላ ስላሉት ዓፄ ልብነ ድንግል ከላይ ስሙን የጠቀስነውን ዮሐንስ

(1) አልቫሬጽ ምዕ. 92
(2) ገጽ 251 ቍጥር ፪
(3) ከስታንሆፕ ጠጕር ቀራጭ ነበር ይለዋል የፖርቱጋሎች ዠግንነት ገጽ 14

ቤርሙዴዝን በዚህ በመከራ ሰዓት ወደ ፖርቱጋልና ወደ ሮማ ሊቀ ጳጳስ ዘንድ ሄዶ በቶሎ የወታደር እርዳታ እንዲያመጣላቸው ላኩት ። ዮሐንስ ቤርሙዴዝም እንደ ኤው. ቁጥር ፲፭፻፴፭ (እንደ ኢ.ት. ቁጥር ፲፭፻፳፯ - ፳፰ ዓ. ም.) ከኢትዮጵያ ተነሥቶ ወደ ሕንድ ለመሄድ አስቦ መርከብ ስላጣ በሱዳን በኩል አልፎ የቱርኮች መቆጣጠር በጥብቅ በሚያሰጋበት ሰዓት በግብጽ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (1) ። ከዚያም እንደምንም መርከብ ተፈላልጎ ወደ ኢጣልያ አገር ደረሰ ። በዚያም የቀድሞው የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቀሌምንጦስ ፯ኛ ሞተው እንደ ኤው. ቁጥር ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ጳውሎስ ፫ኛ ስለተተኩ ለኚሁ ላዲሱ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በኢትዮጵያ ግራኝ አህመድ ያደረገውን ሁሉ ተርኮ በቶሎ እርዳታ እንዲልክ ሊቀ ጳጳሱ የፖርቱጋልን ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛን ያሳስቡ ዘንድ ለመነ ።

ንጉሠ ነገሥቱ ለሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና ለፖርቱጋል ንጉሥ ሁለት የሚያሳዝኑ ደብዳቤዎች ጽፈው ለቤርሙዴዝ መስጠታቸው ሲታወቅ የደብዳቤዎቹን ቅጅ በአማርኛ እዚህ ላይ ትርጉማቸውን ማሥፈር ታሪኩን እንደሚያሟላው የታወቀ ነበር ። ዳሩ ግን ትርጉሙን በላቲንም በኢጣልያም በፈረንሳዊም ቋንቋ ተጽፎ አላገኘሁትም ። በ፲፮ኛውና በ፲፯ኛው መቶ ዓመት የጳጳሳቱ የግንኙነት ማስረጃ ከኢትዮጵያ ጋር በሚል ርእስ ባጻፉት ውስጥ ረኔ ለፌቨር ብዙ ደብዳቤዎች ሲያውፍሩ እነዚህ ደብዳቤዎች ስለሌሉ በቤተ መዛግብቱ አለመገኘታቸውን ያስረዳል ።

ISIC

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ሮማና ፖርቱጋል ሄዶ እርዳታውን ካመጣና በመጨረሻ ካፄ ገላውዴዎስ ጋር በሃይማኖት የተነሣ ተጣልቶ ከተመለሰ ወዲህ የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ ባጭሩ ስለራሱም ስለመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ሁኔታ ራፖር ጻፍልኝ ብሎት በፖርቱጋልኛ አጽፎት ይኸው ራፖር የኢትዮጵያና የአርመን የክርስትና ታሪክ ብሎ ላክሮዝ እንደ አው. ቁጥር በ፲፯፻፴፩ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ከሥር የተላከበትን ሁኔታ በፖርቱጋል የጻፈው ትርጉሙ በፈረንሳዊ ቋንቋ ይገኛል ። በአማርኛ ሲተረጐም ቃሉ እንደዚህ የሚል ነው ። «ኢትዮጵያን የሚገዛው ንጉሠ ነገሥት እናዲንገል (ልብነ ድንግል) ይባላል ። ጻድቅና ጥሩ ክርስቲያን የሆነ መስፍን ነው ። አቡነ ማርቆስ የሚባሉት ፓትርያርክ (ግብጻዊው ጳጳስ) እሞት አፋፍ ላይ ስለሆኑ በርሳቸው እግር እኔ ያገሪቱ ፓትርያርክ እንድሆን የልማዱን ሥነ ሥርዓት ፈጽመው በጵጵስናው ሥፍራ እንዲያስቀምጡኝ ንጉሠ ነገሥቱ ለምኗቸው እሺ ብለው ፈጸሙ ። እኔም ይህ ነገር የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ የጳጳሳት ሁሉ አለቃ በሆነው በሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት እንዲጸድቅ ያስፈልጋል ብዬ ንጉሠ ነገሥቱ ለኔም ለርሱም ላገሪቱም ይበጃልና ታዛዥነቱን ለመግለጽ ወደ ሮማ እንድሄድ ከዚያም ወደ ፖርቱጋል መጥቼ ከአልቫሬዝ ጋር የመጣው ከዚህ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ የላከው ዜጋው ስሙ ታጋዛቮ (ጸጋ ዘአብ) ወደሚባለው ሄጂ ፍጻሜውን እንድመለከት (እንድመረምር) ፈቀደ ።

(1) Histoire de l'Abissinie-A.H.M. Jones-E.Monroe ገጽ 115። ቤርሙዴዝ የሄደበትን ዘመን በፖርቱጋሎች ዝግጅነት ላይ ሊትማን 1530 (1522) ያሉት ስሕተት ይመስለኛል ።

እኔም በብዙ ችግር በጳውሎስ ፫ኛ ዘመን ጵጵስና ሮም ደርሼ በመልካም ተቀ ብለው ይገፔ የመጣሁትን ሹመት በኔው ጥያቄ አጽድቀው የእስክንድርያው ፓትር ያርክ እኔን የኢትዮጵያ ፓትርያርክና ጳጳስ ብሎ እንዲሾመኝ ፈቀዱ ። ከዚያ ወደ ፖርቱጋል መጥቼ (1) በቻልታው ፲፪ ዓመት ሙሉ የተቀመጠውን (ጸጋ ዘአብን) አገኘሁት ። በቸልተኝነቱ ንጉሠ ነገሥቱ ልብነ ድንግል ከእምባሳደርነቱ እንድሽ ረውና እሥሬ ወደ ኢትዮጵያ እንድወስደው አዞኝ ስለነበረ ይኸንኑ ትእዛዝ የሚያ ስረዳውን ደብዳቤ ሰጥቼው ተቀብሎ ሳመው ። የኔንም ሹመት ካወቀው በኋላ እንደ ጳጳሱ እንደ በላዩ ቆጥሮ እጄን ሳመ ። እንዲትም ቃል ሳይተነፍስ ሥፍራውን ስለለቀቀልኝ ከዚያ እንዳገሩ ልማድ ሁለቱንም እጁን በሁለት ሰንሰለት አሠር ሁት (2) በኋላ ግን በንጉሡ (በዮሐንስ) ልመና ሰንሰለቱ እንዲወድቅለት አደረ ግሁ ።

የንጉሠ ነገሥቱ መልእክት የሚያመለክተው አንድ የፖርቱጋል መስፍን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ሴት ልጆች አንደኛዪቱን አግብቶ በሁለቱ ነገሥታት ልጆች ጽኑ ጋብቻ ምክንያት ከፖርቱጋል ንጉሥ ጋር ዘለዓለማዊ ወዳጅ ነት እንዲመሠረት ፤ ከነዚህ ጋብቻ የሚወለደው ልጅ በኢትዮጵያ ዙፋን እንዲቀመ ጥና ዝምድናው ለዘላለም እንዲቀጥል ፤ ለሮማው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ታዛዥ እንዲ ሆን ፤ ከዚሁ ጋር አያይዞ የኢትዮጵያ መንግሥት አገሩን የዘይላ ንጉሥ (3) ስለወረ ረበት የሚከላከልበት የፖርቱጋል ወታደር የፖርቱጋል ንጉሥ እንዲልክለት እየለ መነ በበኩሉ ለዚህ ውለታ ብዙ ገንዘብ በቀላሉ የሚከፍል መሆኑን ፤ ከዚህም ጋር ከርሱ በፊት የነበረው ንጉሥ ኤይታሌ በላሌ (Eytale-Belale) (4) አድርጎት እን ደነበረው ዓባይን ገድቦ ግብፅን ለማጥፋት (በውኃ ጥም ለመግደል) ጉብታ የሚ ቆርጡ ሰዎች (መሐንዲሶች) እንዲላክለት» ነው ሲል ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በዚህ በጻፈው ራፖር ላይ ያረጋግጣል (5) ።

ከዚሁ አያይዞ የንጉሠ ነገሥቱን ጥያቄ በመቀበል የፖርቱጋል ንጉሥ ፬፻፶ ወታደሮች (HARQUE BUZIERS) መሐንዲሶች (PIONNIERS) ተሰጥቶት አዲስ የሕንድ እንደራሴነት ከተሾመው ከዶን ጋርሲያ ደ. ኖራንሃ ወይም ኖሮንሃ ( Don Garcias de Noronhas ) ጋር እንዲሄድ ፈቅዶ ትእዛዝ መስጠቱን ። ዳሩ ግን ከዚሁ ከንጉሡ እንደራሴ ጋር ወደ ሕንድ ሊሄድ ሲዘጋጅ በመካከል በሕ መም መውደቁንና በዚህ ምክንያት ለመታከም በፖርቱጋል አገር ሙሉውን

(1) እዚህ ላይ አያትምን አገኘሁ ይላል የዮሐንስ ፫ኛ አያት ዶም ፌርናንዶ የቬዝ መስፍን ባሁኑ ሰዓት በሕይወት ያለ አይመስልም ።

(2) በቀራኛ መሆኑ ነው ያለዚያ ሁለቱንም እጅ ባንድ ሰንሰለት ለማሠር አይበቃምን ?

(3) ግራኝ አህመድንና የሐረሩን ሱልጣን ፖርቱጋሎች የዘይላ ንጉሦች ይሏቸዋል ።

(4) ዓፄ ዳሊበላ ማለቱ ሳይሆን አይቀርም ።

(5) Histoire du christianisme d'Ethiopie ገጽ 74 - 160 ። Etudes sur l'histoire d'Ethiopie. ሬኔ ባሴት ገጽ 152 ቍጥር 176 ።

ዓመት መቆየቱን በሚቀጥለው ዓመት ካዬ ልብነ ድንግል ዘንድ ተልከው ሊፈል ጉት ከመጡት አንቷን ፌርናንዴዝ ጋስፓር ሱሪያኖ ከሚባሉት ከሁለት የአርመን ተወላጆች ጋር በንጉሡ የጦር መርከብ ተሳፍሮ መሄዱን ሕንድ ሲደርስ የንጉሡ እንደራሴ ጋርሲያ ደ ኖሮንሃ መሞቱን ከዚያ በሚቹ እግር የተተካው ዶን እስጢፋ ኖስ ዶጋማ እንደፈተኛው እንደራሴ ሳይተጋበት ስለቀረ የዚህን ጉዳይ በመጠባ በቅ መቆየቱን እየዘረዘረ ጽፎታል (1) ።

ከኢትዮጵያ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. እ. አው. ቀ· የሄደው ይኸው ቤርሙዴዝ በመ ርከብ ተሣፍሮ ከሊስቦን ወደጎአ (ሕንድ) ከጎአ እንደ ኤው. ቀ·ጥር ፲፭፻፴፮ ዓ.ም. ዓፄ ልብነ ድንግል ከሞቱ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ከወታደሮቹ ጋር ያመጣጣቸውን ሁኔታ ያደረጉትንም ጦርነት ባፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ላይ እንመለከታ ለን ። አሁን ግን ከኢትዮጵያ ሄዶ እርዳታ ይዞ እስኪመጣ ድረስ ያለፈው ጊዜ ስድ ስት ዓመት ግድም ነው ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ዓፄ ልብነ ድንግል ያለረዳት ብቻቸ ውን ከግራኝ እየተከላከሉ እርዳታው ምጥዋ ከመድረሱ ከስድስት ወር በፊት ሲሞቱ ደንበኛው እርዳታ የደረሰው ለልጃቸው ለዓፄ ገላውዴዎስ ነው ። ስለዚህ ይኸን በሥፍራው ባፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ላይ እስክንመለከት ድረስ አሁን ቤርሙዴዝ አውሮፓ በነበረበት ጊዜ ግራኝ አህመድ ከአዶሉ ሞት ወዲህ በትግሬና በቤገምድር የሚቀጥለውን ወረራ የሕዝቡን የማያቋርጥ መከላከል በት ግሬ የተነሣውን ረሃብና በሽታ ፤ የአምባ [illegible]ን ውድቀት ፤ በጣና የገሊላን መዘ ረፍ፤የንጉሡን ልጆች የፈቅጦርን ሞትና የሚናስን መማረክ በየምዕራፉ እናንብብ ።

## ምዕራፍ ፹፱

## በትግሬ ረሃብና በሽታ ተነሥቶ እስላሞችን እንደፈጀ (፲፭፻፳፯ ዓ. ም.) — በትግ ሬና በሐማሴን የተደረገው ሹም ሽር

ግራኝ ወረራውን ከዠመረ እንሥቶ እስኪሞት ድረስ በጠቅላላው ያለው የአሥራ አምስት ዓመት ዘመን ለክርስቲያኖች የመከራና የእልቂት ዘመን መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በርሱ አንጻር ይኸው ዘመን ለእስላሞቹና ለመሪያቸው ሙሉ ደስታ ሊሰጥ አልቻለም ። ሞት ሞትን ይስባል መግደል መገደልን ያስከትላል እንደሚባለው ምንም መጠኑ ቢለያይ ከክርስቲያኖቹ ወገን ብዙ ሕዝብ ቢሞትም ከእስላሞቹ ወገ ንም ሞቱ አልቀረም ። በተሸናፊነት ምክንያት የሞት ሚዛን በተሸናፊዎቹ በክርስ ቲያኖቹ ላይ በብዛት ቢደፋም አሁን ደግሞ ረሃብና በሽታን አምጥቶ እስላሞቹን በመፍጀት እግዚአብሔር በአሸናፊዎቹ ላይ ሚዛኑን ለማስተካከል የፈቀደ ይመስ ላል ።

በአለፈው በተደረጉት ጦርነቶች ከእስላሞቹ የጦር አለቆች የክርስቲያኖቹ

(1) ገጽ 99 - 101

የጦር አለቆች በብዛት የሞቱ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ሆኖም በ፲፰፻፹፬ ዓ. ም. ገራድ አህሙሹ ፤ ገራድ ማታን ፤ አውራይ ኡስማን አምባ ማሼን ግርኜ ከሞቱ ወዲህ በቅርቡ ከላስታ ወደ ትግሬ በሚጓዙበት ጊዜ መቁት ላይ በ፲፰፻፹፮ ዓ. ም. በመስከረም ወር ከደገልሃን ጦር ጋር በተደረገው ውጊያ የግራኝ የወንድሙ ልጅ ዘሀርቡይ መሞቱን እንዳነበብነው በዚሁ ዓመት መጨረሻ በሰኔ ወር ከሁሉ የግራኝ የጦር አለቆች ብልጫ ያለው ወዚር አዶሌ ሲሞት አሸናፊውና ድል አድራጊው ግራኝ አህመድ በጠቅላላው የድል አድራጊነቱን ጣዕም በደስታና በሰላም መካከል እንደልቡ እንዳላጣጣመ የታወቀ ነው ።

በተለይ ደግሞ ያሁኑ የ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. ለግራኝና ለጦሩ የመዓትና የችግር ዘመን መሆኑን በያለበት ብዙ እስላሞች በበሽታ ማለቃቸውን ዓረብ ፋቂህ ሳይሸሽግ ያመለክታል ። በዚህ በሽታ የተነካ የተራውን ሰው እልቂት ወደ ጐን አድርጎ ከታወቁት ውስጥ የሞቱትን ከዚህ እንደሚከተለው ይዘረዝራል ።

፩ኛ. ከድል ወንበራ የተወለደው አህመድ ነጋሽ የተባለው የግራኝ ልጅ ።

፪ኛ. ከበለው ነገድ የሆነው አውራይ አቡበክር የደብረ ሊባኖስን ገዳም ካለቃው ተደብቆ ሄዶ እሳት ለኩሶ ያቃጠለው ።

፫ኛ. ገራድ ሲሙ (ስምዖን) የከዳተኛው የወናግ ዣን ልጅ ራሱ ከዳተኛ ፤ አዝማች አዳሉን አታሎ ለግራኝ የገባና የግራኝን ጦር እየመራ የባሌን ተከላካይ ጦር ደምስሶ ከፍ ያለውን የባሌን ያውራጃ ግዛት ለግራኝ ያሳመነ ።

፬ኛ. ታውዚ የምትባለው የአዶሌ ሚስት ።

፭ኛ. ገራድ አብድ ኢን ናስር ከሚስቱ ከቢልቂሣህ ጋር ።

መቼም ለግራኝ ከነዚህ ከሞቱት ውስጥ ምናልባትም ገና አድጎ ጣሙን ካላወቀው አህመድ ነጋሽ ብሎ ከሠየመው ሕፃን ልጁ የበለጠ የሚያሳዝነው የአብድ ኢን ናስር ሞት ሳይሆን አይቀርም ። አብድ ኢን ናስር በፍጹም ልቡ በፍጹም ኃይሉ ግራኝን ለማገልገል ቆርጦ የተነሣ ፤ ሕይወቱን ለግራኝ የወረራ ምኞት የሠዋ ሰው መሆኑን ለማወቅ ወደኋላው ተመልሶ አንባቢ ይህ ሰው ባለፈው የፈጸመውን አገልግሎት ያስታውስ ይሆናል ። የባደቴን ፤ የሸምብራ ኩሬን ፤ የዝሆን ዱርን ፤ የባሌን ፤ የዋሰልን ጦርነት ሁሉ በቀጥታ እየተዋጋ ተካፍሏል ። በዚህ ሁሉ አገልግሎቱ ገራድ ተብሎ ያን ጊዜ ታላቅ ግዛት የነበረውን የጋንዝን (1) አውራጃ ተሾሞ ነበር ። ብዙ ጊዜ ለግራኝ እንደዋና ጸሐፊ እንደታማኝ ግምጃ ቤት እየተቆጠረ የምርኮ ሀብት በርሱ እጅ ይቀመጥ ነበር ። በሸዋ የእንደገብጣንን (የዛሬው አዲስ ዓለም አካባቢ) ቤተ ክርስቲያን ከአቃጠለ ወዲህ በአማራ አገር የገነተ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ዘርፎ ያቃጠለ ፤ ግራኝ ንጉሡን በመዘጋና በደምቢያ በሚያባርርበት ግንባር ቀደም ሆኖ በጥብቅ ንጉሡን በባሕር ዳር አጠገብ ለመማረክ ከአብሳማ ኑር ጋር ይጣጣር የነበረው እርሱ ነው ።

ስለዚህ በዚህ ሁሉ ችግርና እልቂት ምክንያት ብዙ እስላሞች ማለቃቸውን

(1) ጋንጽ አንዳንድ ጊዜ ጋንዝ ቢጋፋትና በእናርያ በጉራጌና በሐዲያ መካከል ያለ ነው ዛሬ ግንዋ የምንለው ከዚያ የመጣ ይሆናል ።

የተመለከቱ እስላሞች ይኽ መዓት የመጣብን የክርስቲያኖቹ አምላክ ተቆጥቶ ነው ብለው በማመን በቅርብ የሰለሙት ወደ ክርስትና መመለሳቸውን ፤ ከእስላሞ ቹም ውስጥ የፈራቀሃም ሱልጣን ወንድም ሳይቀር ከእስላምነት ወደ ክርስትና መዞሩን ካመለከተ በኋላ የዓረቡ ጸሐፊ አያይዞ በዚህ ጊዜ የጭንት በቅሎም አህያም አልቆ እስላሞቹ ወዲያና ወዲህ ሲዘዋወሩ ከእስላሞቹ አብዛኞቹ ስንቃቸውን በራሳ ቸው መሸከማቸውን ይገልጻል (1) ። ጸሐፊው ከዚሁ አያይዞ በዚህ የተነሣ ግራኝ አህመድ እስላሞቹን ሁሉ እፊቱ ሰብስቦ «በረሃብና በበሽታ ምክንያት የደረሰብ ንን ተመለከታችሁ ። እንግዲህ ይኽን አገር ብንለቅ ይሻላልና ወደየትኛው አው ራጃ ብንሄድ እንደሚሻል አሳባችሁን አስታውቁኝ» ብሎ እንደ ጠየቃቸው ፤ እነር ሱም «መወሰንና ማዘዝ ያንተ ጉዳይ ስለሆነ እኛ ወደምትሄድበት እንከተልሃለን» ብለው እንደመለሱለት ፤ እርሱም «የቤገምድር አገር ብዙ ሀብትና መልካም ነገር የሞላበት አገር ስለሆነ ወደዚያ እንሂድና መቀመጫችንን በዚያ እናድርግ ከተማና መስጊድ ሡርተን በዚያው እንቀመጥ ሌላውንም አውራጃ ማስገበር ሲያምረን ጓዛ ችንንና ቤተ ሰባችንን በዚያ አስቀምጠን ወደፈቀድነው አገር መዝመት እንችላ ለን» ቢላቸው ሁሉም «መልካም ነው» ብለው እንደመለሱለት ያመለክታል ።

ከዚህ በኋላ ወደ ቤገምድር የመሄዱ ነገር በዚህ ዓይነት ከተወሰነ ወዲህ የትግ ሬን ግዛት ከመልቀቁ በፊት ከዚህ እንደሚከተለው ሹም ሽር አደረገ ።

፩ኛ. ለተስፋዊ ሡራዬን

፪ኛ. ለአፍራ ባሕር ነጋሽነት

፫ኛ. ለዘር ሡናይ (ዘርዓ ሡናይ ?) ሐማሴንን

፬ኛ. ለሱልጣን አህመድ ቤን ኢስማኤል የድሆኖን (የእርኪቆን ወደቦች)

፭ኛ. ለነዚህ ሁሉ ጠቅላይ የበላይ ገዥ በቅርብ ጊዜ የአዶሌን ገዳይ ተስፋ ልዑልን ከገደለ ወዲህ የአዶሌን የወዚርነት ማዕርግ ለሰጠው ለወንድሙ ለአቡን ልጅ ለወ ዚር አባስ ሰጠው (2) ።

ይሁን እንጂ አባስ ከግራኝ ጋር ወደ ቤገምድር አብሮ መጓዙን እንመለከታለን። እዚህ ላይ እንደምንመለከተው ከወዚር አባስ በቀር ሁሉም የተሾሙት ያገር ተወላጆች ናቸው ። ሡራዬን የተሾመው ተስፋዊ የታማኙ የተስፋ ልዑል ዘመድ የከሐዲው የቴዎድሮስ ወንድም መሆኑን ባለፈው አንብበናል ። አፍራ ምንም ዝር ዝሩን ባናውቀው በቀይ ባሕር ዙሪያ ባንዱ ወረዳ የባላባትነት ደረጃ የሚያጣ አይ መስልም ። ዘርዓ ሡናይም የሐማሴን ተወላጅ እንጂ ከእስላሞቹ ወገን አለመሆኑን ስሙ ራሱ ያስታውቃል ። ሱልጣን አህመድ ቤን ኢስማኤል የዳህላቅ ባላባት ከዚህ በፊት እንደ አው. ቀ. ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ዦአኦ ሲልቬይራ ወደ ዳህላቅ የመጣ ጊዜ እምኖ ለፖርቱጋሎቹ ከገባ በኋላ ከድቶ ብዙ ፖርቱጊዞች የገደለ ፤ በኋላ ደግሞ እንደ ገና ሮድሪግንና አልቫሬዝን ከነጓደኞቻቸው ለመውሰድ ምጥዋ በመርከብ ለመ

(1) ዓረብ ፋቂህ ....... ገጽ 448 - 449

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 449 - 450

ጣው ለሄክቶር ደ ሲልቬይራ ገብቶ በሰላም የተገናኘና ያስተናገደ ነው (1) ።

እርሱና እርሱን የመሳሰሉት የዳህላቅ የአርኪቆ ባላባቶች (ናይቦች) ቱርክ ሲያይል ለቱርክ ፤ ፖርቱጋሎች በርትተው ቱርክን ሲያባርሩ ለነርሱ በተረፈ ደግሞ ከሁለቱም ይልቅ ያገር ተወላጁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲያይል ለርሱ እየገበሩና እየታዘዙ የሚኖሩ መሆናቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

ስለዚህ አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ የግራኝን ማየል ሲረዳው ለግራኝና ለምክትሉ ለወዚር አባስ ገብቶ ታማኝነቱን ከመግለጽ ጋር በውጊያም በአስተዳደርም ስላገለገለ በዚያው በይዞታው በደሆኖ (የዛሬው አርኪቆ) ተሾሟል ማለት ነው ።

እንደዚህ አድርጎ የሚቃወሙትን ከማጥፋት ጋር የሚታመኑትን ያገር ተወላጆች መሾሙ ባሁኑ ሰዓት የቆየውን የአስተዳደር ፖለቲካ ለውጦ የቅኝ አገረ ገዥዎች ብዙ ጊዜ የሚያደርጉትን የአገዛዝ ዘዴ ተከትሏል ማለት ነው ። እስካሁን ድል እያደረገ በሚይዛቸው በደቡቡ ክፍል ያገር ተወላጁን ቢበዛ ምክትል እያደረገ በበላይ ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚሾመው የራሱን ከሐረር አብረው የዘመቱትን ሹማምንት ነው ። ከሐዲዎቹ እነአናንያ ፤ እነሲሙ የገራድነት ማዕርግ ቢይዙም ያንዳንድ ጥቃቅን ወረዳ እንጂ እንደ ደዋሮ ፤ እንደባሌ ፤ እንደፈጠጋር ባሉት ታላላቅ አውራጃዎች በሙሉ ሥልጣን አልተሾሙም ።

አሁን ግን ፬፻፸ ወገን በግዛት በመቆየትና በመዝናናት በሌላ ወገን ረሃብና በሽታ አስቸግሮት አውራጃውን እንዲለቅ ስለአስገደደው በሹመት ያገር ተወላጁን በማስደሰት ግራኝ አህመድ ከመረብ ወዲያ ባለው በሠራዬ ፤ በሐማሴን ፤ በቀይ ባሕር አካባቢና በወደቡ ላይ ያገር ተወላጁን እየመረጠ ሾመ ። በዚህም ላይ እነዚህ የተሾሙት ለንጉሡና ለሃይማኖታቸው ከታመኑት ዘመዶቻቸው ጋር ደም ስለተቃቡ ለኔ መታመንና የኔን አገዛዝ ማጽናት የነርሱን የገዥነት ሥልጣን ሊያረጋግጥላቸው ስለሚችል ለራሳቸው ሲሉ ከመጭው የክርስቲያን አጥቂ ጋር ራሳቸው ይከላከላሉ ፤ ያለዚያም እርስ በርሳቸው ከተላለቁ በኋላ ቢሸነፉም በመጨረሻ እኔ ተመልሼ የጐበጠውን መልሼ አቀናዋለሁ የሚል ስሜት በግራኝ አህመድ አእምሮ ውስጥ አይጠፋም ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፯

### የዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ መዳከም — በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች የስም አጠራር ልዩነት — በግድም ያዒ ልብነ ድንግልና የኤሚር ስምዖን ጦርነት ። (፲፭፻፳፯ ኅዳር ፲፱ ቀን ) የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት ።

ሙሉ ስሙ ሺሃብ ኤዲን አህመድ ኢብን አብድል ቃድር ባጭሩ ዓረብ ፋቂህ (ሕግ አዋቂው ዓረብ) የሚባለው እስካሁን በየምዕራፉ ስንጠቀምበት የመጣነው

(1) በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ገጽ 450 የረኔ ባሴት ማስታወሻ ቍጥር 2

ጸሐፊ ጦርነቱ ከተገፐመረበት ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. አንሥቶ እስከዚህ እስከ ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. ድረስ በሸዋ ፤ በሸዋ ዙሪያ ፤ በአይፈርስ ፤ በሽምብራ ኩሬ በባሌ ፤ በዝሆን ዱር ፤ በዋስል ፤ በቤተ አምሐራ ፤ በትግሬ ፤ በዓባይ ዳር ለተደረገው ጦርነት ሁሉ ለአጻጻፉ አልፎ አልፎ የንግግር ወዝ እየሰጠ አንዳንድ ጊዜም የተዋጊን ወታደር ቊጥር የውጊያን ቦታ የገዳይንና የሟችን ስም እየጠቀሰ ብዙ ጊዜ የራሱን ወገኖች አንዳንድ ጊዜም እንደ ሐቀኛ ጸሐፊ ከክርስቲያኖቹ ውስጥ እንደ አዝማች አዳሉ ያሉት የሠሩትን ጀብዱ ሳይደብቅ በዝርዝር ይጽፍ እንደነበረ አንባቢ ራሱ ይገነዘብለታል ።

የኛ ታሪክ ነገሥት ተራው ሕዝብ በማይገባው ቋንቋ በግዕዝ ለዚያውም ባንድ መስመር ጠቅሶ ያለፈውን እርሱ ግን በአብዛኛው ጦርነት ላይ ራሱ እየተገኘ በሌለበት ደግሞ ከተዋጊ እየጠየቀ የክርስቲያኖቹን ወገን ከምርኮኞች ወይም አውቀው ከገቡት እየተመራመረ በዓረብኛ በሰፊው ይጽፍ ከነበረው ላይ ወደ አማርኛ እየተረጐምን ያቀረብነውን አንባቢ ተመልክቶታል ።

አሁን ግን በዚህ ዘመን የተነሣው ረሃብና በሽታ ያድክመው ወይም እርጅና ይጫነው ወይም መሰልቸት ይደርበት ወይም ግራኝ ባንድ ምክንያት አስቀይሞት የጽሕፈት አምሮቱን ያጥፋበት አይታወቅም በአጻጻፉ ከአምና ከ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ዠምሮ ከእንደርታውና ከአጋሜው ጦርነት ወዲህ በአገላለጡ ደከም እያለ ሄዷል ። የፊቱንም ወደኋላ ማስቀደም ይታይበታል ። ለምሳሌ ንጉሡ ከነሻውል ጦርነት በፊት ከኤሚር ስምዖን የተዋጉትን እርሱ ግን ይህን ጦርነት በኋላ አድርጎ ጽፎታል ። ታሪክ ነገሥቱ ከኤሚር ስምዖን ጋር የተዋጉ ጊዜ የሞቱትን ሰዎች የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሲጠቅስ እርሱ ግን የስምዖንን ጦርነት ካወሳ በኋላ የቀረውን ዘሎታል ።

ታሪክ ነገሥቱ በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ኅዳር ፲፱ ቀን ንጉሡ ከኤሚር ስምዖን ጋር ተዋግተው በውጊያው ማዕቀበ እግዚእ (1) ጽራግ ማሠሬ ተክለ ሥሉስ ፤ አቤቶ ቴዎድሮስ መሞታቸውን በዚሁ ጊዜ የአክሱም የሃሌሎ ፤ የበንኰል ፤ የሲጋሶ ፤ የደብረ ከርቤና ሌሎችም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸውን በግዕዝ ይጠቅሳል (2) ።

የዚህን ጦርነት ዓረብ ፋቂህ በበኩሉ ባጭሩ እንደዚህ ብሎት አልፏል ፤ «አህመድ ከኤሚር ሻምሱንና ከጦሩ ጋር በጐጃም ተገናኘ እርሱንም በግድም ትቶት ነበር ። ያበሻ ንጉሥ ብዙ ጦር ይዞ ቢመጣበት አርባ ፈረሰኞች ይዞ ገጥሞ አባረረው ። ብዙ ሀብትና ወታደርም ማረከበት» (3) ።

በቀድሞ አጻጻፉ ቢሆን ይህን ንጉሡ ራሳቸው ከኤሚር ስምዖን የተዋጉበትን እነአቤቶ ቴዎድሮስ የሞቱበትን ጦርነት ዓረብ ፋቂህ የሟችንና የገዳይን ስም እየ

(1) አንዳንዱ ማዕቀ እግዚእ ስለሚል ሙሴ ሬኔ ባሴት በገጽ 452 ቊጥር 1 ካመለከቱበት ላይ ትርጉሙን በስሕተት የጌታ ቀጣ ብለውታል ። ማዕቀበ እግዚእ የጌታ ወታደር ወይም ጌታ የሚጠብቀው ማለት ነው ትግሬዎች ዕቁበ እግዚእ እንደሚሉት ፤

(2) ታሪክ ነገሥት ገጽ 93

(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 465 - 466

ጠቀሰ ከብዙ ታሪካዊ አድራጐት ጋር እየጨመረ አስፋፍቶ ይተርክልን ነበር ። እነ ዲያውም የገላቢጦሽ በዚህ ላይ ከዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ የኛው ግዕዝ እንደተሻለ ይታ ያል ።

የኛ የግዕዙ ስምዖን ያለውን ዓረብኛው ሻምኡን እንዳለው ተመልክተናል፤ መቼም የአገርና የሰው ስም አጠራር እንዳገሩ እንደፊደሉና እንደልማዱ ነው ፤ ለምሳሌ እኛ ወደ ግሪክኛ አስታከን ሰሎሞን ስንል ዓረቦቹ ሶሊማን ይላሉ ፤ ይኸ ንኑ ስም ይሁዲዎች ደግሞ ሽሎሞ ይሉታል ። እኛ አብርሃም ስንል ዓረቦቹ ኢብራ ሂም ይሉታል ። ስለዚህ የግዕዝኛውና የዓረብኛው አጠራር ባንዱ ሰው ስም ላይ የሚለያየው በዚህ ምክንያት ነው ።

የስም ልዩነት የየአገሩን በየመልኩ ካልሰሙትና ካላዳመጡት አዳምጠውም ካላገናዘቡት አንዱ ሰው በልዩ ልዩ መንገድ ተጠርቶ ሲገኝ ብዙ ሰው ይመስላል ፡ ለምሳሌ ጴጥሮስን ወገኖቹ አይሁዶች ኬፋ (ደንጊያ) ብለውታል ። ይኸው ስም በሮ ማይስጥ (ላቲን) ፔትሩስ ፤ በጽርዕ (ግሪክ) ፔትሮስ ፤ በኢጣልያ ፒዬሮ ፤ በኤስፓ ኝና በፖርቱጋል ፔድሮ ወይም ፔሮ ፤ በፈረንሳዊ ፒዬር ፤ በእንግሊዝኛ ፒተር በስ ላቭ ሕዝብ ዘንድ ፔትሮቪች ፤ በዓረብኛ ቡትሮስ ይሉታል ።

እኛ ግን ሰብአ ሊቃናት የሚባሉት በግብፅ የሚቀመጡት ፸፪ የአይ ሁድ ሊቃውንት (282.283 ዓመት ከክር. በፊት) ከዕብራይስጥ ብሉይን ወደ ጽርዕ ስለተረጐሙት እኛም ወደ ግዕዝ የተረጐምነው ከጽርው ስለሆነ በመጽ ሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ስሞች የግላችንን አጠራር ሳንለቅ ወደ ግሪኮቹ አጠ ራር እያስጠጋን አብርሃም ሰሎሞን ጴጥሮስ ስምዖን እንላለን ።

ጦርነቱ የተደረገበትን አገር ግዕዙ በአምሐራ ሲል የዓረቡ ጸሐፊ በግድም ያለ ውን ተመልክተናል ። የዚህም ልዩነት ምንም ያህል አልተራራቀም ። ከጋላ ሥሪት በፊት ከአማራ ሳይንት ዠምሮ ግድም የዛሬው የወሎ ግዛት ጭምር እስከ መንዝ ድረስ በጠቅላላው የአማራ አገር ነው ። በዝርዝር ግን በዚህ በሰፊው የአም ሐራ አገር አማራ ሳይንት ቤተ አምሐራ ዋስል ፤ ግሼን ፤ ግድም መንዝ እየተባሉ ወረዳዎቹ ይዘረዘራሉ ። ስለዚህ ግዕዙ በጠቅላላው ስም አምሐራ ያለውን ዓረብ ፋቂህ ግን በተለይ ጦርነቱ የተደረገበትን የግድምን ወረዳ መጥቀሱ ነው ።

በጦርነቱ የሞቱትን እላይ እንዳመለከትነው ዓረብ ፋቂህ አልጠቀሰም ግዕዙ ግን ማዕቀበ እግዚእንና ጽራግ ማሠሬ ተክለ ሥሉስን ፤ አቤቶ ቴዎድሮስን ጠቅ ሷል ። የመዠመሪያዎቹ የቤተ ክህነት ሰዎች ስለሚመስሉ (1) ከውጊያ ይልቅ በን ጉሡ አጠገብ ተገኝተው ወይም ተማርከው የተገደሉ እንጂ ሲዋጉ የሞቱ አይመስ ሉም ። ወይም አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክህነቱንና የቤተ መንግሥቱን ተግባር አንዱ ሰው ደራርቦ ስለሚይዝ እነዚህም ታላላቅ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሰዎች እየተዋጉ ሞተው ይሆናል ።

(1) ጽራግ ማሠሬ አንዳንድ ጊዜ ጽራጅ ሌላ ጊዜ ራቅ ማሠሬ ይባላል ፤ ዋና ተግባሩ በንግሥ ቀን ለን ጉሡ ዘውድ ስለሚደፋ ክብሩና ማዕርጉ ከፍ ያለ ነው ። የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ምዕ. ፳፮ ገጽ ፻፵፱ - ፻፶፫

ከነዚህ ጋር የሞተው ቴዎድሮስ በስሙ ላይ የተሰጠው የማዕርግ ስም አቤቶ፣ የሚል ስለአለበት ከንጉሣዊ ቤተሰብ ውስጥ ይመስላል ። የንጉሡ ያዔ ልብነ ድንግል አያት ዓፄ በእደ ማርያም ራስ ገዚት (ራስን የምትገዛ) ከምትባለው ዕቁባታቸው ቴዎድሮስን መውለዳቸው በዜና መዋዕላቸው ተጽፏል (1) ። እርሱ ይሁን ወይም ሌላ አይታወቅም ። አቤቶ የሚባለውም ሥያሜ አንዳንድ ጊዜ ከነጋሢ ለማ ይወለዱ ለታላላቅ ሰው ልጆች ሲሰጥ በየዜና መዋዕል ላይ አልፎ አልፎ ይታያል ።

ባለፉት ዓመታት በሸዋና በአምሐራ አውራጃዎች የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት እንደዚሁም በሺሬ የደብረ ዓባይን ቃጠሎ ታሪክ ነገሥቱ ዝርዝራቸውን ካወሳ ወዲህ አሁን ደግሞ ከአክሱም ጋር የሃሌሎ ፤ የበንኰል ፤ የሊጋሶ ፤ የደብረ ከርቤ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸውን ሲያወሳ እነዚህ አብያተ ክርስቲያን ያሉበትን ልዩ የወረዳ ስም የተካያቸውን ስም የተተከሉበትን ዘመን በቤተ አምሐራ እንደነበሩት አብያተ ክርስቲያን ተለይቶ በታሪክ ነገሥቱ አልተጻፈም ። ዓረብ ፋቂህማ በዚህ ጊዜ አጻጻፉ እየተዳከመ እንደመሄዱ መጠን በፍጹም አላወሳቸውም ።

መቼም ታሪክ ነገሥት የሚባለው ባንድ ስም ሲጠራ አጻጻፉ ያንዱ ከሌላው ይለያያል አንዱ የዘለለውን ሌላው ይጨምራል ። አንድ በአማርኛ የተጻፈ አዲስ አበባ በቤተ መጻሕፍት የሚገኝ አክሱም፻SI፷ቃጠለ አሌሎን (ሃሌሎ ያለውን ?) ደብረ መንገሻን በንኰልን ደብረ ከርቤን አቃጠላቸው ይላል ። ሌላ ደግሞ አንድ ሮማ ከቫቲካን በፎቶ ኮፒ አስነሥቼ ያገኘሁት ታሪክ ነገሥት በ፳፫ኛው ገጽ ላይ "...... ዓምደ ጽዮን ፴ ዓመት ነገሠ በርሱ ዘመን ያቡነ ተክለ ሃይማኖት ልጅ (2) አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በንኰል በሚባለው በትግሬ ነበሩ ። እርሳቸውም ባንድ ቀን ስድስቱ ከዋክብት ተብለው የተሠየሙትን የዋልድባውን አባ ሳሙኤልን የቈየጻውን ሳሙኤልን ፤ የጣሬጣውን ሳሙኤልን ፤ የጉራንቋን ዮሐንስን ፤ የባልታርዋ ታዴዎስን ፤ የማንደምባውን ያሳይን ፤ የጕጉቤውን ያፌቅረነ እግዚእን ...... አመነኰሷቸው" ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ በ፳፬ኛው ገጽ ላይ ያምደ ጽዮን ልጅ ሰይፈ አርዕድ ፳፰ ዓመት ነገሠ እርሱም እስከ ትግሬ ድረስ ሄዶ ከበንኰል ደብር ላይ ወጥቶ "አባ መድኃኒነ እግዚእ አርጅተው ደቀው (ከዊኖ ድቁቀ) አግኝቷቸው ቡራኬ ከርሳቸው ተቀበለ" እያለ በግዕዝ ቋንቋ ይተርካል ።

ስለዚህ የደብረ በንኰል ተካይ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ወይም አያቱ ይኩኖ አምላክ ይሆናል ማለት ነው ። የገዳሙ የታወቁት አቅኚ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ መሆናቸው ነው ። ዓፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፳፫ኛው ዓመት በ፲፭፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ለነዚሁ ገዳማት ርስተ ጉልት መትከላቸውን በገለጹበት ጽሑፍ ላይ የነዚህ አድባራት ስማቸውና የአበምኔቶቹ (ያለቆቹ) ስም ከሌሎች አድባራት ጋር ተጨማምሮ እንደዚህ ሲል ተጠቅሶ ይገኛል ።

(1) ያዔ በእደ ማርያም ዜና መዋዕል በኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ገጽ 251

(2) የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ለማለት ነው ።

አባ ተንሥእ መድኅን ዘደብረ በንኰል (ደብረ ክርቤ)
” ገብረ መርዓዊ ” ሃሌሉያ (ሃሌሎ)
” አሥራተ ጽዮን ” ሲጋሶ

ከነዚህ ውስጥ የበንኰልን መምህር አባ ተንሥእ መድኅንን ባንድ ቦታ ላይ ንቡረ ዕድ ዘበንኰል ብሏቸው ይገኛል (1) ።

ከነዚህም ጋር ፤

አባ ማዕቀበ እግዚእ ዘደብረ በቍር ወደብረ በርበሬ
” ተክለ ጊዮርጊስ ዘደብረ ጽዮን
” ንፍታሌም ዘደብረ መግራ
” በኩረ ጽዮን ነጋዴ ዘደብረ አይስማ ዘአባ ፊልሞና
ሠርፀ ድንግል ዘዳሞ
” እስጢፋኖስ ዘመካነ ያክስ

እያለ ከዘረዘረ በኋላ እነዚህ ሁሉ ጉልት እየተሰጣቸው ሲተክሉና ሲገደሙ በውስጣቸው የሺሬ ሹም የእንደርታ ሹም የአጽቢ ሹም የስሐርት ሹም የተንቤን ሹም የአጋሜ ሹም የአምባ ሠነይት ሹም እንዳይገቡ ስለሚከለከል እነዚህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት አብዛኞቹ በትግሬ ግዛት በያለበት ይገኛሉ ማለት ነው ። ከነዚህ ውስጥ ያ[illegible]ዚ የተቃጠሉትንና የዳኑትን ወይም ተቃጥለው ከዚያ ወዲህ በተነሡት ነገሥታት ዘመን ተመልሰው የተሠሩትን አላውቅም ።

በተረፈ ታሪከ ነገሥቱ ወተዓብዓ ንጉሥ ምስለ ስምዖን (ንጉሡ ከስምዖን ተዋጋ) ብሎ አሸናፊውንም ተሸናፊውንም ሳይለይ ያለፈውን ዓረብ ፋቂህ ንጉሡ ብዙ ጦር ይዞ ቢሄድበት ኤሚር ሻምኡን አርባ ፈረሰኛ ይዞ ገጥሞ አሸንፎት ብዙ ከብትና ሰው ማረከበት ያለውን አንብበናል ።

በዚህ ዓይነት ግራኝ በትግሬ አገር በነበረበት በጸለምት በወገራ በመዘጋ እየተ ላለፈ ከነአዝማች ሻውል ጋር በሚዋጋበት ጊዜ ንጉሡ ሁል ጊዜ ግራኝ ያለበትን ወይም ያመራበትን በታማኞቻቸው እያሰለሉ የርሱ ጦር እንደ ግድም ራቅ ብሎ የሚገኘውን ለመደምሰስ ፈትነዋል ማለት ነው ።

ነገር ግን ሁልጊዜ ምንም በዙሪያቸው ታማኝ ጦር ከነአለቃው ባይጠፋ ከዳተኛውም በዚያው ልክ ስለሆነ በዚህም ላይ እስካሁን የቆየውን የንጉሡን ሕይወት መከባከብ ስለአለ ትንሽ እንደተቆራቆሱ ከመከከላቸው እነ አቤቶ ቴዎድሮስ እነ ጽራግ ማሠሬ ተክለ ሥሉስ ሲወድቁ ጦርነቱን ለመቀጠል ሲፈለግ በንጉሡ ሕይ ወት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሞት አደጋ በማመዛዘን በምክር ከጦርነቱ ቦታ አፈግፍገው ይሆናል ።

(1) Liber Axum - C. Rossini ገጽ 38 - 39

## ምዕራፍ ፶፩

## ግራኝ አህመድ ከትግሬ ወደ ቤገምድር ሲዛወር ከሻውልና ከአዝማች ዮሐንስ ጋር ያደረገው ጦርነት (፲፭፻፳፯ ሚያዝያ)

ግራኝ አህመድ በትግሬ ሕዝቡን ረሃብና በሽታ ስለጨረሰበት የሚወዳቸውን ሹማ ምንቱን እነአብድ ኢን ናስርን ስለገደለበት ከትግሬ በመዘጋ በወገራና በሰሜን በኩል አድርጎ እግረ መንገዱን በፊቱ ያጋጠመውን የክርስቲያን ጦር እየወጋ ራቅ ወዳለው ወደ ሰሜን ተራራ ጦር እየላከ እያስመታ ጉዞውን እንዳሰበው ወደ ደምቢያ አደረገ ።

ስለዚህ ጉዳይ ታሪክ ነገሥቱ ከነአቤቶ ቴዎድሮስ ሞትና ከነሃሌሎ ቃጠሎ አያይዞ እንደዚህ ይላል «መለሳይ (ግራኝ) በመዘጋ በኩል ወደ ወገራ ሄዶ ከተስፋ ኢየሱስ ልጅ ከሻውል ጋር ተዋግቶ ሻውል በሚያዝያ ፲፪ ቀን ተሸነፈ ። በዚህ ጦር ነት አዝማች ዮሐንስና ገንዘይ እንደዚሁም ቡሳ ሞቱ ከዚህ በኋላ ሰሜንን ደምቢ ያንና ቤገምድርን ገዛቸው» (1) ።

በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ግራኝና የጦር አለቆቹ በኢትዮጵያ ላይ ገዥነት እንደተሰማ ቸው ቤተ ሰቦቻቸውን ከሐረር አስመጥተው እንዳረፉ ወደ ሐድያ ወደ ጉራጌ እስከ ወላሞና ሲዳሞ ከምዕራብም እስከ ወሊጋና እስከ እናርያ እስከ ጋፋት ድረስ ባለው ወረዳ ከተስፋፉ በኋላ ወደ ትግሬ መዝመታቸውን በመንገድ አምባ ግሼንን ፪ኛ ጊዜ ወግተው ሳይሳካላቸው ስለቀረ [illegible] ሄደው የላሊበላን አብያተ ክርስቲያ ናት መበዝበዛቸውን በ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. ትግሬ ገብተው በአጋሜ ፤ በእንደርታ ፤ በተ ምቤን ተዋግተው በአክሱምና በመዘጋ አድርገው በግሥጋሤ ዓባይ ዳር ንጉሡን ሊማርኩ እንደነበረ ፤ ይኸም ሳይሳካላቸው ከቀረ በኋላ በደምቢያና በፎገራ ዕረ ፍት ካደረጉ በኋላ እንደገና ወደ ትግሬ ተመልሰው ሳለ ተስፋ ልዑል አዶሌን አባስ ደግሞ ተስፋ ልዑልን እንደምን እንደገደለ አንብበናል ።

ስለዚህ አሁን በትግሬ ረሃብና በሽታ ሰውን ባጠቃበት ጊዜ ግራኝ ከነጦሩ ከዚህ ቀደም በሄደበት በጸለምትና በመዘጋ አድርጎ ከዚህ በፊት አምናውን ያገኑን ልምላሜና ሀብት በዓይኑ ዓይቶ ወዳደነቀው ወደ ደምቢያ ጉዞውን ገሠመረ ማለት ነው ።

እላይ እንዳመለከትነው ሲሄድ እግረ መንገዱን በሺሬ ከአዝማች ዮሐንስና ከሻውል ጋር መዋጋቱን ታሪክ ነገሥቱ ከዚህ በላይ የጠቀሰውን ዓረብ ፋቂህም እዚህ ላይ ትንሽ ሰፋ አድርጎ እንደዚህ ሲል ተርኮት ይገኛል «. . . . . . እሳላሞቹ ሁሉ ወደ ይማም ከመጡ በኋላ ወደ ቤገምድር ጉዞው ተገመረ . . . . . . ዮሐንስ የሚባል መኾን ወደ ተቀመጠበት ቦታ ይማም ሄዶ በጧት ደረሰ ። ወደ ተራራ የሚ ያስወጣው በር ሁለት ብቻ ስለነበረ ጦሩን ከሁለት ላይ ከፍሎ ለፈረሰኞቹ ጥሩ

(1) መለሳይኒ ዓርገ እንተ መዘጋ ወወገራ ፣ ወተፃብአ ምስለ ሳውል ወልደ ተስፋ ኢየሱስ ወተመውዓ ሳውል አመ ፲ወ፪ ለሚያዝያ ወሞቱ አዝማች ዮሐንስ ወገንዘይ ወቡሳ ወመለኮን ለሰሜን ወለ ደምቢያ ወለቤገምድር ወነበረ ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 329 ፤

ጥሩ ግላስ የተጫኑትን ፈረሶች . . . . . . . ለእግረኞቹ የወርቅ አምባር ሸልሞ
አድሎ ሲጨርስ የእግረኛው ጦር ከፈረሰኛው ወደ ፊት ቀድሞ ወደ ተራራው መሳ
ጣት ሲጀምር ከላይ ያሉት ክርስቲያኖች ደንገያና ጦር እየወረወሩ ይወጉዋቸው
ጀመር እስላሞቹም ዝም ብለው ወደፊት ገፉ ።

የኑብያና የሐመጃ ሰዎች ከክርስቲያኖቹ ጋር ሆነው እስላሞቹን ይወጉ ስለነ
በረ ጦርነቱ ከቧት ጀምሮ እስከ ጀምበር ጥልቂት ቆየ ። የሺሬ ሰዎች በጦር ውር
ወራ ብልሃታቸውና ጉብዝናቸው በሀበሻ አገር የታወቀ ስለሆነ በእስላሞቹ ላይ
ብዙ ጉዳት አድርገው ቁስለኛም በረከተ ። ስለዚህ ይማም ወደማታ የቁስለኛውን
ብዛት ተመልክቶ ሰው ሁሉ ወደ ቤገምድር ተራራ ሥር ሄዶ እንዲሠፍር አዘዘ

ከዚሁ አያይዞ ታሪክ ነገሥቱ ያለውን በማጽደቅ ዓረብ ፋቂህ ግራኝ ከዚህ
ተራራ ሥር ወደ ቤገምድር ለመሄድ መዘጋ አገር ደርሶ የራማዳንን ጾም በመዘጋ
አገር እንደፈታ የመዘጋም ሕዝብ እስላሞቹን ደህና አድርጎ ከአስተናገዳቸው
በኋላ ጉዞውን ወደ ቤገምድር ለመቀጠል ሲጓዝ በተስፋ ኢየሱስ ልጅ በሻውል አዝ
ማችነት ውስጥ ዮሐንስ የጸለምቱ ሹም ፤ ከቤገምድሩና ከወገራው ሹም ጋር ተባብ
ረው ለመዋጋት በመንገድ ላይ ሆነው መጠባበቃቸውን ካመለከተ በኋላ ስለውጊ
ያው እንደዚህ ይላል ።

«በዚ[illegible]ከንያት ይማም ጦሩን እሁለት ክፍሎ አንዱን ለራሱ አስቀርቶ
እፊት ሲጓዝ ፪ኛውን ለወዚር አባስ ሰጠውና ከኋላ ደጀን ሆኖ እንዲከተለው አደ
ረገ ።

ይማም ወደፊት ሲጓዝ ክርስቲያኖቹ እያዙት ጠባብ መንገድ ላይ ደረሰ ። ክር
ስቲያኖቹም ወታደራቸውን አሰልፈው ወደፊት መጡና ውጊያው ተጀምሮ
ከጧት እንሥቶ እስከ እኩለ ቀን ተዋጉ ። ነገር ግን ውጊያው ፍሬውን አልሰጠም ።
በዚህ ጊዜ አንድ አዝማች ተክሉ የሚባል እስላም ወደ ይማም መጣና ከዚህ ከያ
ዝነው መንገድ ሌላ የተራራ መንገድ አውቃለሁ ብሎ ነገረው ።

ስለዚህ የቀረውን ጦር ለወዚር ሙጃሂድ ሰጥቶ እዚሁ ሆነህ ጠብቅ ብሎ አዘዘ
ውና እርሱ ይኸን የተባለውን መንገድ ለመመርመር ፭ የተመረጡ ፈረሰኞች አስከ
ትሎ በድብቅ ሄደ ። በደረሰም ጊዜ በሩን ይዘው የሚከላከሉትን ክርስቲያኖች
አገኘ ። ከነርሱም መካከል ነበልባል የሚመስሉትን ፈረሶቻቸውን እንደያዙ አዝ
ማቹ ሻውልና ዮሐንስ ነበሩ ።

በዚያን ጊዜ ይማም የባሕር ወታደሮቹንና የእግረኛ ወታደሮችን እፊት አስቀ
ድሞ እስላሞቹ ውጊያውን ሲጀምሩ ከዚያም ፈረሰኞቹ ተከታትለው ገቡበትና
ውጊያ ሆነ ። ከዚያ ክርስቲያኖቹ ሊሸሹ ሲሉ የእስላሞቹ ፈረሰኞች ዞረው ከበቡዋ
ቸው ፤ ወዚር ሙጃሂድም ያንኑ የመጀመሪያውን መንገድ ይዞ በበኩሉ ይወጋቸው
ጀመር ። በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖቹ ተዘበራርቀው ወዲያና ወዲህ ሲሉ እስላሞቹ እየ
ተከታተሉ ግማሹን ሲገድሉ የቀረውንም ሲማርኩ ዮሐንስ ከዛፍ ላይ ወጥቶ ለማም
ለጥ ሲሞክር የወጣበት ዛፍ ተሰበረና ወድቆ ሞተ ።

ይማም ዮሐንስ ወደ ወደቀበት ሥፍራ ሄዶ የእግረኛ ወታደሮቹን ቢልክ ሹማ

ምንቱን በዚያ አገኙዋቸውና ሁሉንም ማረኩዋቸው ። ከነርሱም መካከል የአዝ ማቹ የሻውል ወንድም ገንዘይ የሚባል ነበር ፤ በማን (በአማን ?) የቤገምድር ሹምና የሠራዬ ሹም ሌሎችም ፳ የሚሆኑ ሹማምንት ተማረኩ ። ከነርሱ ውስጥ ወደ ስሜን ከሄደው ከሻውል በቀር አንድም ያመለጠ የለም . . . . . .» (1) ።

ዓረብ ፋቂህ በሺሬ ላይ በሚገኘው ተራራ ላይ በተደረገው ጦርነት ክርስቲያ ኖቹ በእስላሞቹ ላይ ብዙ ጉዳት በማድረጋቸው ግራኝ እነሱን በጦር ኃይል መፍጀ ትም መማረክም አቅቶት ትቶት ጉዞውን ቀጥሎ ወደዚህኛው ከሻውል ጋር ወደተ ደረገው ጦርነት ሲመጣ በዚያኛው ጦርነት ላይ የጸለምቱ ሹም ዮሐንስ መዋጋቱን ከተረከ በኋላ በዚህኛው ጦርነት ጊዜ ከዛፍ ላይ ወድቆ የሞተው ዮሐንስ መሆኑን አይለይም ።

ነገር ግን ጸለምት ወገራ ሺሬ ወሰነተኞች ሆነው ከወዲህም ከቤገምድር ጋር ስለሚዋሰኑ የአራቱም አውራጃ ሹማምንት ለየብቻ በመዋጋት ፈንታ በሻውል ውስጥ ሆነን ተባብረን እንመክት ብለው በምክር ተባብረው ተዋግተው ይሆናልና በፊተኛውም በአሁኑም ተዋግቶ የሞተው ያው አንዱ ዮሐንስ የጸለምቱ ሹም ይሆ ናል ።

በዚህ ምዕራፍ ቀደም ብሎ በተደረገው ጦርነት የሺሬዎቹን በጦር ውርወራ ያላቸውን ዘዴ በአመሰገነበት ላይ ዓረብ ፋቂሂ ከሺሬዎቹ ጋር የኑብያና የሐመጃ ሰዎች አብረው ይዋጉ ስለነበረ ጦርነቱ ከጧት ዠምሮ እስከ ዠምበር ጥልቀት ቆየ ያለውን እናስታውሳለን ።

ISIC

በውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ ነገዶች ሳይዘረዘሩ በጠቅላላው የዛሬው ሱዳን ቀድሞ ኑብያ ይባል ነበር ። ነገር ግን በውስጡ ያለው የነገድ ሕዝብ ተለይቶ ሲጠራ በኑብያ (ወይም በዛሬው ሱዳን ውስጥ) የሰርበት ፤ የዛግዋ ፤ የአልዋ ፤ የኑብያ ፤ የአበሻ ፤ የብጋ (በጅያ) የሳራስኒ ፤ የግብፅ ሕዝቦች አሉበት በነዚህም ጐን ብሌሚይ ኖባድ ማኩሪት የሚባሉ አሉ ። በነዚህ ትልቅ አውራጃዎች ውስጥ ዳር ሮዝሬይ የሚባል ወረዳ በዚህም ወረዳ ውስጥ ሐሙጅ የሚባሉ ሕዝቦች አሉ (2) ።

በዚህ በአሁኑ ጦርነት እነዚህ የኑብያና የሐሙጅ ሕዝቦች በክርስቲያኖቹ ጐን ሆነው መካፈላቸው የጸለምቱ ወይም የሺሬው ገዥ ያን ጊዜ ይጠቀልላቸው ስለነበረ በትእዛዝ ይካፈሉ ወይም ክርስቲያኑ የኑብያ ሕዝብ ከግብጽ በ፲፩ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ የመጣ ጦር ነዋሪ ሆኖ ሲያሰልመው ግማሹ ግን የጥንት የክርስትና ሃይማኖቱን ሳይለውጥ እስከዚህ ጊዜ ደርሶ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያን ክርስቲያ ኖች እስላሞቹ እንዳጠቁዋቸው ሰምተው ለእርዳታ የተዋጉ ይሁኑ ለይተን አናው ቅም ። እስካሁን ድረስ የጽሑፋችንን ማነስ አንባቢ እንደሚረዳው ጊዜና አስረጅ ጽሑፍ ወደፊት እስኪገልጸው ድረስ ይኸንንና ይኸን የመሰለውን ሁሉ በጥያቄ ጉዳዩን አንጠልጥለን ለማለፍ ግዴታችን ነው ።

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 452 - 453
(2) Storia della Nubia Christiana UGO Monneret....chap. XIV-XVI : Geographie d'Ethiopie-A. d'Abbadie ገጽ 59

## ምዕራፍ ፺፪

### የአይሁድ የክርስቲያንና የእስላም ልዩነቱና ግንኙነቱ — ስለፈላሾች ።

የግራኝ ጦር ወደ ትግሬ በገባ ጊዜ የእስላምን ሃይማኖት ከቀድሞ ዠምሮ ያቀፉት የበለው ነገዶች ከግራኝ ጋር በኅብረት ተገናኝተው በምን አኳኋን መሣሪያ እንደ ሆኑት አንብበናል ። አሁን ደግሞ የዚሁ የአሸናፊው የግራኝ ጦር በትግሬና በጸ ምት አልፎ ፈላሾቹ ወደሚገኙበት ወደ ወገራ ወደ ሰሜን ሲመጣ ፈላሾቹ ባለፉ ከክርስቲያኖቹ ጋር ባላቸው ቂም የተነሣ ለግራኝ አግዘው ክርስቲያኖቹን ወጉ ዋል ። አንዱን እግዚአብሔርን በ፫ ሃይማኖት ከፋፍለው የሚያመልኩት ፈላሾቹ ክርስቲያኖቹና እስላሞቹ በመካከላቸው በጠቅላላው በመሠረቱ ከሴም ወገን የ ሬዱ ሆነው የዘርና የቀለም ልዩነት የለባቸውም ። በዚህ ዓይነት እንዲያውም በሥጋ ዘመዳሞች ናቸው ማለት ነው ።

ነገር ግን ከምንጩ ለበጎ ተግባር የተመሠረተው ግብረ ገብነትን ሕግን የሚ ስተምረው ሃይማኖት የአስተማሪነት መስመሩን እየለያየ በሦስት ዓይነት በሦስት የዘመን ወቅት ስለአመጣው ሦስቱን የሃይማኖት ልዩነት የተቀበሉት ወገኖች ጠበ ኞችና ባላጋራዎች ሆኑ ። ይሁዲ ፣ ክርስቲያን እስላም ሦስቱም ወገኖች ከሥር ከመ ሠረት ዓለም ጣዖት አምላኪ በሆነበት ሰዓት እሥራኤላዊው ሙሴ (በዕብራይ ስጥ ሞሽ) በISIC ረተው በኦሪቱ መጻሕፍትና ባንድ አምላክ እምነት ሲገናኙ ሦስ ቱም መልሰው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዓይነት ተለያይተው ጠበኞች ሆነዋል ።

### ፩ኛ. አይሁድ ወይም እሥራኤላውያን

ዓለም ሁሉ በፀሐይና በጨረቃ በልዩ ልዩ ሥነ ፍጥረት ብዙ ጊዜም በነገሥታትና በታላላቅ ሰዎች በሚያመልክበት ዘመን መካከል ሙሴ ወገኖቹን ይዞ ከግብፅ የኤር ትራን ባሕር ተሻግሮ ሲና በረሃ በገባበት ሰዓት እውነተኛውን ሃይማኖትና ሕግ ያሉ በትን ፲ቱ ቃላትን ከእግዚአብሔር መቀበሉን ለወገኖቹ አሳመነና ዝርዝር ሕግ ያለ በትን ኦሪት የሚባለውን መጽሐፍ አዘጋጅቶ ለወገኖቹ ተወ ። ይህ ሕግ ኦሪት በሚ ባል ሥያሜ ተሠይሞ በውስጡ አምስት ክፍል አለው ። ከዚህ በፊት እንዳመለከት ነው ፡-

ሀ. ኦሪት ዘፍጥረት የሚባለውን የአዳምን ዘር በኖህና በአብርሃም በኩል የወረደ ውን የዘር መስመር ይተነትናል ። አዳምን የሰው ዘር መዠመሪያ እንደ ማድ ረጉ መጠን የቻይናን ፤ የሕንድን ነገድ ሲጨምር አይታይም ። የፈረንጆችን የነገድ አባት ያፌት ፤ የጥቁርን ካም ፤ የብጫን ሴም አድርጎ መድቧል ።

ለ. ኦሪት ዘፀዐት በሚባለው ላይ የእሥራኤሎቹ ከግብፅ አወጣጣቸው ተተርኮ በት ይገኛል ። በዚህም ላይ ለሕግ ሁሉ መሠረት የሆኑት አትግደል ፤ አትስ ረቅ . . . . . . የሚሉት አሥሩ የሕግ ቃላት ይገኙበታል ። ሙሴ የነበረበት ዘመን ፲፫ኛው መቶ ዓመት ከክርስትና በፊት ሲሆን ከርሱ በፊት ፺፬ ዓመት የሚቀድመው ሐሙራቢ የሚባለው የባቢሎን ንጉሥ ሕዝቡ የሚተዳደር

በት ሕግ ስለአወጣ የሙሴ ፲ቱ ቃላት እንደመገመሪያ ሕግ ሊቆጠሩ አይች ሉም ። የሙሴ በኋላ እንደመምጣቱ መጠን ከሐሙራቢ ሕግ በተሻለ አኳኋን ቀርቧል ። ሐሙራቢ አባቱን የመታ ልጅ እጁ ይቆረጥ ያለውን (1) ሙሴ አባትህን እናትህን አክብር ብሎ ለስለስ አድርጎ አቅርቦታል ።

ሐ. ኦሪት ዘሌዋውያን ነው ። ሌዋውያን የእሥራኤል ልጅ የሌዊ ተወላጆች ናቸው (2) እነርሱም የቤተ ክህነት ወገኖች ሲሆኑ ራሱ ሙሴና ወንድሙ አሮን የሌዊ ወገኖች ናቸው ። በዚህ መጽሐፍ ካህናቱ የሚተዳደሩበት ወግና ሥርዓት ለእግዚአብሔር ቁርባን የሚያደርሱበት ፣ የሚገርዙበት ፣ የሚበላ ውና የማይበላው እንስሳ ተለይቶ የተዘረዘረበት ይገኛል ።

መ. ኦሪት ዘኁልቍ ነው ። አርእስቱ እንደሚያመለክተው ፲፪ቱ የእሥራኤል ነገ ዶች እየተለዩ ለየብቻ በስምና በቍጥር እየተመዘገቡ የተጻፉበት ነው ።

ሠ. ኦሪት ዘዳግም ነው ። ይኸም እሥራኤሎች ከግብፅ ወጥተው ወደ ምድረ ከነ ዓን (የዛሬው ፓለስቲን ወይም ፭ኤሎቹ የያዙት ጭምር) የገቡ ጊዜ በድጋሚ የተሰጣቸው ሕግ ያለበትና የቀድሞውን አጥብቀው እንዲከተሉ ለማሳሰቢያ የተጻፈበት ነው ።

አምስቱ የኦሪት መጻሕፍት እነዚህ ናቸው ። የአገራችንና የውጭ ሊቃውንት አንዳንድ ጊዜ የኢያሱን ፣ የመሳፍንትን ፣ የሩትን መጻሕፍት በመጨመር ፰ቱ በሐ ውርተ ኦሪት ይሏቸዋል ። የሆነ ሆኖ ከነዚህ፴፱ቱ በብሉይ ውስጥ የሚገኙትን የሳሙ ኤልን የነገሥትን የዜና መዋዕልን ፣ የነህምያንና የዕዝራን ፣ የኢዮብን ፣ የዳዊትን መዝሙር የሰሎሞንን ምሳሌ የነቢያቱን ትንቢት ሁሉ ለሃይማኖትም ለፍልስፍ ናም ለሞራልም መመሪያ አድርገው ይዘዋቸዋል ። ከዚያም ወዲህ አይሁድ በየዘ መኑ በመሻሻልና በመጨመር ለብሉይ አዳዲስ ትርጓሜ በዝርዝር ያዘጋጁበት ታልሙድ የሚባል መጽሐፍ አላቸው ።

ስለዚህ ከእው ሁሉ በፊት ሙሴ ይኸን የኦሪት ሕግ በጽሑፍ ከአወጣ ወዲህ በመገመሪያ ባንድ አምላክ በማምለክ አይሁድ ቅድሚያ ስለአላቸው ክርስቶስ ከነርሱ ወገን ስለተወለደ በክርስቲያን ዓለም ዘንድ ከፍ ያለ መንፈሳዊና ሥጋዊ ግምት አግኝተውበታል ። ይኸ ግምት ግን ክርስቶስን ከአሰቀሉበት ጊዜ ዠምሮ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ተመልሶ ፈርሷል ። አይሁድ ክርስቶስን ሰቀሉ በማለት ፈንታ አሰቀሉ የምንለው እነርሱ ይሰቀልልን ብለው አቤት ባዮች ናቸው እንጂ በቀጥታ ሰቃዮች አይደሉም ። በቀጥታ ለመስቀልም ሥልጣንና መብት አልነበራ ቸውም ። በነርሱ አቤቱታና ክስ ክርስቶስን የሰቀሉ አገረ ገዥዎቹ ሮማውያን ናቸው ። ነገር ግን «ይሰቀልልን ! ይሰቀልልን !» እያሉ በመጮህ "ካልሰቀልኸ ውም የቄሣር ወዳጅ አይደለህም" ብለው በማስፈራራት ኃላፊነቱን ስለወሰዱ የክ ርስቲያኑ ዓለም በአነጋገር ልምድ ጭምር የክርስቶስ ሰቃይ ያላቸውን የኛዎችም "አይሁድ ሰቃልያነ ክርስቶስ" በማለት ሲጠሉዋቸው ሲያጥላሏቸው ኖረዋል ።

(1) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጕዬ ምዕራፍ 17 ገጽ 120 - 123
(2) ዘፀዓት ምዕ 2 ቍጥር 1 - 2 ። ዘኁልቁ 23 ቍጥር 14

ስለዚህ አይሁድ እንደ ኦሪት ትእዛዝ አዶናይ ወይም ያህቤ በሚሉት ባንድ አምላክ ብቻ እያመኑ በኦሪት የተጻፈውን ግዝረቱን ይይዛሉ ቅዳሚን ያከብራሉ ። መሢሕ (አዳኝ ወይም የተቀባ) ወደፊት ከመካከላችን ይነሣል ብለው ይጠብቃሉ ። የክርስቶስንም አምላክነቱንም መሢሕነቱንም ፈጽሞ ይክዳሉ ። እንኳን የመሢሕነት እንደ ሙሴ እንደ ኤልያስ ወይም እንደ ኢሳይያስ የነቢይነት ደረጃ እንኳን አልሰጡትም ። በእነሱ አቤቱታ ስለተሰቀለ ፤ በርሱ መስቀል ምክንያት አይሁድ በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ ብዙ ሥቃይና ስደት ስለገጠማቸው እንዲያውም በክርስቶስ ላይ ጥላቻ አላቸው ለማለት ይቻላል ።

## ፪ኛ ክርስቲያን

፪ኛው መደበኛ ሃይማኖት የክርስትና ሃይማኖት ነው ። ከሙሴ በኋላ ፲፭፻ ዓመት ቆይቶ ክርስቶስ ተወልዶ በነዋሪው ኦሪት ላይ አዳዲስ ትምህርት እየጨመረ አስተምሮ በሙሴ ፲ቱ ቃላት ላይ ፮ ቃላተ ወንጌል የሚባሉትን አክሎ ያስተማረውን እርሱ በቀጥታ በእጁ የጻፈው ጽሑፍ ባይተውም የርሱ ተከታዮች ከአንደበቱ ሰምተው የጻፉት የአራቱ ወንጌላውያን ጽሑፍ ወንጌል የሚባለው ለክርስቲያኖች መሠረታዊ የሃይማኖት መጽሐፍ ሆነ (1) ። በርሱም ላይ ጸሐፊው ሉቃስ ይሁን ወይም ጳውሎስ[illegible]ከክል ያልታወቀው የሐዋርያት ሥራ ፤ የጳውሎስና የጴጥሮስ የያዕቆብና የይሁዳ መልእክቶች ከዮሐንስ ራዕይ ጋር ተጨምሮ በጠቅላላው ሐዲስ የሚባለው መደበኛ መጽሐፍ ሆነ ። ከዚያም አይሁዶች ታልሙድ የሚባለውን እንደጨመሩ የክርስቲያኖቹም ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈወርቅና እነ ቄርሎስ ሌሎቹም በየመልኩ የጻፉት የሊቃውንት መጽሐፍ የሚባለው ቍጥሩ በየጊዜው እየተባዛ ሐዲሱ እንዲጸና እንዲበረክት አስፋፍተውታል ።

ሐዲስ ከመጣ ወዲህ በብሉይ ተጽፎ የነበረው ዝርዝር ሕግና ወግ እያደር ተሻረ ። ጳውሎስ ለግዝረት ዋጋ በማሳጣት በግዝረት መንግሥተ ሰማያት አንገባም ባለመገረዝም አንቀርም ብሎ ስለአስተማረ (2) ግዝረት በብዙ የአውሮፓና የአሜሪካ ክርስቲያኖች ዘንድ ቀረ ። በኛ ዘንድ ግን ልማድ ሆኖ እነሆ ኑሮውን ይቀጥላል ።

በኦሪት ቅዳሚ እንዲከበር ታዞ የነበረው የኛ አምላካችን አዳኝ መሢሐችን ለኛ ሲል ሞቶ ከተቀበረበት የተነሣው እሑድ ለት ስለሆነ በቅዳሚ ፈንታ እሑድ ይከበር ብለው በኒቅያ ጉባኤ በ፫፻፳፭ ዓ. ም. ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት የወሰኑት ጸና ።

በኦሪት ሰውን በምሳሌዬ (በመልኬ) ልሥራ በማለት ፈንታ በምሳሌያችን እንሥራ ብሎ እምላክ በብዛት የተናገረው (3) አብርሃም ቤት ገብተው የተጋበዙት በ፫ት ሰው መልክ ስለተገለጹ (4) በሐዲስ ደግሞ ሂዱ አሕዛብን አስተምሩ በአብና

(1) ከአራቱ አንዱ ማርቆስ ወንጌልን የጻፈው ከጴጥሮስ እየሰማ ነው ይባላል ።
(2) ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕ. 7 ቍ. 19 ገላትያ ምዕ. 6 ቍ. 15
(3) ዘፍጥ. ምዕ. 1 ቍ. 26
(4) ዘፍጥ. ምዕ. 18

በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ብሎ ክርስቶስ መናገሩ በወንጌል ስለ ተገለጸ (1) ይኸን የመሳሰለው አምላካዊ አነጋገር መሠረት ሆኖ አይሁዶችና እስላ ሞች ባንድ አካል ባንድ መለኮት የመደቡትን አምላክ ክርስቲያኖቹ በአካል ሦስት ነቱን (ሥላሴ - አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ) በመለኮት አንድነቱን ተቀበሉ ።

በተግባርም አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ተብሎ በረቀቀ አሳብና ትርጓሜ ከተለየ በኋላ እኛን ለማዳን በአብ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከማርያም ተወልዶ በ፴ ዓመቱ ተጠምቆ ፫ ዓመት አስተምሮ በኋላ በ፴፫ኛው ዓመቱ ላይ በአይሁድ ተይዞ በአገሪቱ የበላይ አስተዳዳሪ በሮማዊው በጲላጦስ የው ሳኔታና የግዴታ ፈቃድ ተሰቅሎ የሞተው ሞቶም የተነሣው ክርስቶስ ከሦስቱ አንዱ ወልድ መሆኑን ክርስቲያኖቹ መሠረት አድርገው ይዘው በኋለኛው ቀን በደጎችና በኃጢአተኞች መካከል ሊፈርድ የሚመጣው እርሱ መሆኑን አምነው ይኖራሉ ።

## ፫ኛ እስላም

፫ኛ ክርስትና በተመሠረተ በ፮ተኛው መቶ ዓመት ላይ የአይሁድንና የክርስ ቲያኖቹን አባባል ፲፭ ዓመታት ሲያጠና የቆየው ማሐመት (ሙሐመድ) ተነሥቶ የእስላምን ሃይማኖት መሠረተ ። የእርሱም ሃይማኖት ከአይሁድና ከክርስቲያን በኋላ በመጨረሻ የተገኘ በመሆኑ ከሁለ§I§ምነት ተውጣጥቶ ለዓረቦች የኑሮ ደረጃና ልማድ ተስማሚ የሆነ ገራገር አረማዊ በቀላሉ ሊቀበለው የሚችል "፩ አምላክ የማይወለድ የማይወልድ የማይሞት ነው" ብሎ ተነሣ ። በ፫ አካላት የተከፈለ በአንድ መለኮት የተዋሐደ ነው ፤ የክርስቶስ ልደቱ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ። መንፈስ ቅዱስ የሚሠርፀው ግማሹ ከአብ ብቻ ነው ፡ ግማሹ ከአብና ከወልድ ነው እየተባለ ከክርስቲያኖቹ በኩል የሚነገረው ስለአልመሰለው ክርስት ናን ሳይቀበል የቆየው የዓረብና የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብ በቶሎ የመሐመድን ስብከትና አባባል ተቀበለው ። ስብከቱም እስከ ሩቅ ምሥራቅ እስከ ኢንዶኔዚያ ደረሰ ፡ በአፍሪካ ሰሜን በተለይ እንደዚሁም በቀረው አፍሪካ ተቀባይ በማግኘት ተስፋፋ ።

የሆነ ሆኖ ሙሐመድ እንደሙሴ እንደ አሪት የአምላክን አንድነት ብቻ አስተ ማረ ። ያምላክን ሦስትነቱን ከሦስቱ አንዱ መወለዱንም መሞቱንም ካደ ። ነገር ግን ከአይሁዶች በመለየት ኢየሱስ ያላባት በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከማርያም ድን ግል የተወለደ ጻድቅ ሰው (ፍጡር) መሆኑን በኋለኛውም ቀን በኃጥአንና በጻድቃን መካከል ሊፈርድ የሚመጣ መሆኑን አምኖ አሳመነ (2) ።

በዚህ ምክንያት እስላሞች እንደ አይሁድና እንደ ክርስቲያኖች የእምነትና የሕግ ሁሉ መደብና መነሻ የሆነውን በጠቅላላው የብሉይን መጽሐፍ ይቀበሉና

(1) ማቴ. ምዕ. 28 ቍ. 19

(2) ቁራን ምዕ. 2 ቍ. 130 ፡፡ ምዕ. 3 ቍ. 37 . 43

የክርስቶስን አምላክነትን የአምላክን ሥላሴነት ስለሚጠቅስ ሐዲስን ችላ ይሉታል ። በርሱ ፈንታ ከክርስቶስ በኋላ መሥራቹ መሐመድ በገብርኤል አማካይነት ከሰማይ ወረደልኝ ብሎ ያስተማረበትን በመቶ አሥራ አራት ምዕራፎች (ሱራት) የተከፈለውን ቁራንን እንደ መደምደሚያ ቅዱስ መጽሐፍ አድርገው በርሱ ይመራሉ ። መሐመድንም እንደ መጨረሻ ነቢይና መሪ አድርገው ተቀበሉ ።

ስለዚህ እስላሞች በአካል በማይከፈል ባንድ አምላክ እምነት ከአይሁድ አንድ ሲሆኑ ክርስቶስን ያላባት የተወለደ ጻድቅ ነው በኋለኛውም ቀን ሊፈርድ የሚመጣ እርሱ ነው በማለታቸው ወደ ክርስቲያኖቹ በአጋማሽ ይቀርባሉ ማለት ነው ።

በነዚህ በሦስቱ መደበኛ ሃይማኖቶች ምክንያት በዓለም የተደረገውን የርስ በርስ ጦርነት ለመተረክ ብዙ ገጽ ያለው መጽሐፍ ሳይሆን በብዙ ቅጽ (ቮሊም) የተከፈለ ብዙ መጽሐፍ ያስፈልጋል ። ፭ኤሎች ያንድ አምላክን እምነት ከመያዛቸው የተነሣ ለድል አድራጊዎቹ መንግሥታት ጣዖት አንሰግድም በማለት በ፭፻፹፯ ዓመት ከክርስትና በፊት ናቡከደነጾር የባቢሎን ንጉሥ ማርኮ ወደ አገሩ ወሰዳቸው ሰሎሞንም ያሠራው ቤተ መቅደስ ፈረሰ ። ከዚያ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ቸርነት ተመልሰው ከተቋቋሙ በኋላ ፪፻፳፭ ዓመት ከክር. በፊት በአንጥያኮስ ፬ኛው ጊዜ ለግሪክ አማልክት አንሰግድም ስላሉ ተፈጁ ። በሮማውያን ዘመን በ፸ ዓመት ከክር. በኋላ እናት ልጅዋን እስክትበላ ድረስ ተከበው ብዙዎቹም በጦር ሠራዊት እየተመቱ አለቁ ። በናቡከደነጾር ጊዜ ፈርሶ ተመልሶ የተሠራውም ቤተ መቅደስ እንደገና ፪ኛ ፈረሰ ። እነሱም በሮማውያኑ ቄሣር ትእዛዝ በየአገሩ ተበተኑ ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ለጣዖት ሲሰግዱ እግዚአብሔር በነቢያቱ አፍ እየተቆጣ መዓቱን ሲልክባቸው የነበረው የገላቢጦሽ ለእግዚአብሔር ብቻ በመስገዳቸው ጣዖት አምላኪዎቹ ነገሥታት ፈጅተዋቸዋል ማለት ነው ።

እስላም በተነሣበት ዘመን ደግሞ ክርስቲያኖቹ የቊስጥንጥንያ ነገሥታት ከደማስቆና ከባግዳድ ከግብፅ ከሊፋዎች ጋር ያደረጉት የሃይማኖት ጦርነት ፤ ከዚያ ደግሞ ኢየሩሳሌምን ለመያዝ በአረቦቹና በአውሮፓ ክርስቲያኖች መካከል የተደረገው የመስቀል ጦርነት ሲበርድም ሲሞቅም ከ፲፻ ፺፮ ዓ. ም. እስከ ፲፪፻፸ ዓ.ም. ድረስ ዘልቋል ።

በክርስቲያኖቹ መካከልም ሃይማኖትና ሥነ ሥርዓቱ ይሻሻል አይሻሻልም ጻድቃን ያማልዳሉ አያማልዱም በማለት ጉዳዩ ከፖለቲካና ከነጋሥያን ዙፋን አወራረስ ጋር እየተጣመረ በአውሮፓ ፫ ጊዜ ታላላቅ ጦርነት ተደርጓል ። አንዳንዱም ጦርነት እስከ ፴ ዓመት (፲፮፻፲፰ - ፲፮፻፵፰) የፈጀበት ጊዜ ብዙ ስለሆነ ሁኔታውን በዚህ ምዕራፍ ላይ ለመተረክ ጊዜ የለም ።

ከሥሩም በክርስቶስ ፪ ባሕርይና ፩ ባሕርይ በመንፈስ ቅዱስ አሠራረጽ በክርስቶስ ዕርገት የመላእክት ጾታ ምንድነው በማለት በየጥቃቅኑ መምህራንና ጳጳሳት በክርክር የሚለያዩበት ጠብ ይኸውም ልዩነት ደጋፊዎቻቸውን ነገሥታት እየሳበ አዋግቷል ።

የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ ከእስክንድርያ በወረሰችው ባንድ የክርስቶስ ባሕርይ እምነት ከአብርሃ ወአጽብሐ ዠምሮ የተቀበለችው እስከዚህ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ደርሶ ከዚያም ግራኝ በዚህ ዘመን ያመጣውን መከራ አልፎ በሰይፍ በትር በጅምላ ያሰለመውም እንደገና እንሠራርቶ ቀደምት ተዋሕዶ ሃይማኖቱን አጥብቆ በመያዝ እስከዚህ ደርሷል ።

የእስላም ሃይማኖት ከቀይ ባሕር ማዶ ከዓረብ አገር በየጊዜው የመጡት ዓረቦች ተክለውት በየጊዜው በሰሜን በደቡቡ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ተስፋፋ ። በቀን ብዛት ባላባትነቱን በይፋት የተከለው ኡመር ወላስማ የሚባለው የእርሱም ተከታዮች ለእስላሙ ክፍል እንደ ንጉሥ ተቆጠሩ ።

የአይሁድ ሃይማኖት በዓለም ላይ ቍጥሩ ትንሽ ነው ። አይሁድም ከአምላክ የተመረጥን ልዩ ሕዝቦች ነን እንደሚሉት ሁሉ ሃይማኖቱንም የግላቸው ሆኖ እንዲቀር በመፈለግ ክርስቲያኖቹና እስላሞቹ በግድም በውድም ሃይማኖታቸውን ሲያስፋፉ አይሁዶች ለራሳቸው አጥብቀው መያዝ እንጂ ዘሩ ከአይሁድ ውጭ የሆነ ሰው ሃይማኖታቸውን እንዲይዝ በፍጹም አይጣጣሩም ።

ስለዚህ ይሁዲ በዓለም ቍጥሩ ትንሽ እንደሆነ በኢትዮጵያም የይሁዲን ሃይማኖት የያዙት በስሜን በወገራ የሚገኙት ፈላሾች ቍጥራቸው ከ፳ ቢበዛ ከ፴ሺ አይበልጥም ይባላል ።

ISIC

ስለክርስቲያንና ስለእስላም ብዙ ጊዜ ስለአነበብን አሁን ፈላሾቹ እንደምን እንደተቀበሉት ከማንበባችን በፊት ባጭሩ ስለፈላሾች አስቀድሞ መጻፍ ለአንባቢ መንገድ ይሰጣል በማለት ከዚህ አስከትለናል ።

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የአገራችን ታሪክ ከንግሥተ ሳባና ከሰሎሞን የተወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ እሥራኤል አገር ሄዶ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ከርሱ ጋር ብዙ የእሥራኤል ተወላጅና ካህናት አብረው ወደ ኢትዮጵያ ስሜን መጥተው ባገር ላይ ካለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተደባልቀው አሪትን እያስተማሩ በልማድም በጋብቻም ተቀላቅለው ሲኖሩ በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን አባ ሰላማ ክርስትናን በኢትዮጵያ ባስገባ ጊዜ የአክሱም ሕዝብ ክርስትናን ሲቀበል ከእሥራኤል ነገድ ከሆኑት ውስጥ እነዚህ ፈላሾች የተባሉት በዚያው በቀድሞው ሃይማኖት በኦሪት ጸኑ ። ክርስቲያኖቹም በቀን ብዛት ቢጨቁኗቸው ከአክሱምና ከዙሪያው እየተነሡ ተራሪማ ወደሆነው ወደስሜን ወደ ወገራ ወደ ወልቃኢት እየተሰደዱ ስለተቀመጡ ስማቸውም ፈላስያን (ስደተኞች) ተባለ ተብሎ በየመጽሐፉ ተጽፏል ።

ይኸን ታሪክ ቤተ ክህነቱም ቤተ መንግሥቱም ራሳቸውም ፈላሾቹም የሚያምኑበት ነው ። ነገር ግን ከዚያ ወዲህ የተነሡ የውጭ አገር መርማሪዎች የይሁዲነት ዘር ያላቸውም የሌላቸውም ከፈረንጅ አገር እየመጡ እስከ ቤገምድር ድረስ እየሄዱ የፈላሾቹን የመልካቸውን ቅርጽ የቋንቋቸውንና የልማዳቸውን ዓይነት በጥናት እያመዛዘኑ በሰጡት አስተያየት ተለያይተዋል ።

እንቷን ዳባዲ ፥ ኮንቲ ሮሲኒ ፥ ገፀሬፍ ሐሌቪ ፥ ሽሎቢስ ፥ ናሁም የሚባሉት ፈላሾቹ ከአገው ሕዝብ በመልካቸው ቅርጽና በደም ግባታቸው የተለዩ ስላይደሉ

በአካል የሴማዊ ዘርነት ይኸውም ማለት እሥራኤልነት የላቸውም ብለዋል ። ስቲ ርን ፣ ፍላድ ፣ ፋይትሎቪች ፣ ራቲዩንስ ሌሎቹ ደግሞ የሴም ወገኖች ናቸው ብለ ዋል (1) ። ብዙዎቹ ደግሞ ፈላሾቹ ሲታዩ ከቀረው የሀበሻ የክርስቲያን ሕዝብ በመ ልክና በቅርጽ በቀለም ምንም ልዩነት ስለማይታይባቸው ፈላሾቹ ከሴማዊው ሕዝ ብም ከአገውም የተደበላለቀ ሕዝብ ነው እንጂ አብዛኛው ሴማዊ አይደለም ። የይ ሁዲን ሃይማኖት በመምህር በኩል ተቀብለውት ይሆናል የሚሉ አሉ ።

ፈላሾቹ የሚገኙበትም ሥፍራ አብዛኛው በቤገምድርና በስሜን ግዛት ውስጥ በተለይ በቋራ ፣ በደምቢያ ፣ በአርማጭሆ ፣ በጠገዴ ፣ በወልቃኢት በስሜን ፣ በወ ገራ በጉንደ መረባ ፣ በጣቁሳ ፣ በአቸፈር መሆኑን የዚህኑ ጉዳይ በጥልቅ ያጠናው (CA.Z. AESCOLY) ያረጋግጣል (2) ።

ይኸም መርማሪ ፈላሾቹ ምንም እንኳን እንደ አይሁድ ባንድ አምላክና በኦ ሪት የሚያምኑ ቢሆኑ እንደ አይሁድም ቅዳሜን ቢያከብሩ ግዝረትንም ቢያጸኑ ባንድ ወገን ደግሞ ከክርስቲያኖቹ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥምቀት ፣ የቁርባን የኑ ዛዜ ሥነ ሥርዓት እንዳላቸው መነኮሳት ቀሳውስት ደባትር እንዳሏቸው እንደ ክር ስቲያኖቹ በግዕዝ ቋንቋ እንደሚጠቀሙ ያረጋግጣል (3) ።

የሆነ ሆኖ ዓረቦች ሰሜን አፍሪካን ግብፅን በወረሩበት ሰዓት ኃይላቸውን በቀይ ባሕር ወደቦች ባሰሙበት በ፰ኛውና በ፱ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ የአክሱም መንግሥት ሲዳበም እንደ አገዎቹ እነዚህም የፈላሻ ዘሮች ከአክሱም ነገሥታት ሥልጣን ውጭ የራሳቸውን መንግሥት አቁመው ጌዴዎን የሚባል አንግሠው እንደነበረ ከርሱም በኋላ የተዋበችው ሴት ልጁ ዮዲት ነግሣ ወደ አክሱም ዘምታ የክርስቲያኑን መንግሥት ገልብጣ የነገሥታቱን ዘር አጥፍታ እንደ ነገሠች በየመ ጽሐፉ ብዙ ጊዜ የተተረከውን ከርሷም ላይ መንግሥትን የዛጉዌ ወገኖች ወስደው እስከ ፲፫ኛው መቶ ዓመት ካስተዳደሩ በኋላ ለዚህ ላሁኑ መንግሥት መሥራች ለሆ ነው ላዔ ልብነ ድንግል የዘር አባት ላዔ ይኩኖ አምላክ መልቀቃቸውን የኢትዮጵ ያን ታሪክ የሚከታተል አንባቢ እንደሚያውቀው የታወቀ ነው ።

እንግዲህ በኢትዮጵያ ክርስቲያናዊው ሕዝብ በክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት በሚገዛበት ሰዓት እስላም በርከት ብሎ የሚገኝበት የሐረር ፣ የባሌ ፣ የአሩሲ ፣ የአ ዳል ወረዳዎች ፈላሻ በብዛት የሚገኝበት የወገራ የስሜን አውራጃዎች አብረው እንደ ክርስቲያኑ ሕዝብ ለነጋሢው እየገበሩ ለተሾመው እየታዘዙ ብዙ ዘመን ኖረ ዋል ። ከመካከላቸውም በመንግሥት የሚሾሙ አሉባቸው ። ነገር ግን አንድ አንድ ጊዜ መጥፎ ሹም በተሾመና ባጉላላቸው ጊዜ ወይም በሃይማኖታቸው ምክንያት "ይህ ፈላሻ ወይም ይኸ ይሁዲ" በመባል መናቅ መጕጠጥ የደረሰባቸው በመንግ ሥት ላይ ይሸፍታሉ ። ይኸም ማንም ሊያደርገው የሚችል ምክንያትን የተደገፈ አሸፋፈት ነው ።

(1) Cahiers d'étude africain Notices sur les Felacha......A.Z. AESCOLY ገጽ 88
(2) " " " " ገጽ 91
(3) " " " " ገጽ 95 - 105

ከዚህም ሌላ በየዘመኑ የክርስቲያን ነገሥታት ደከም ባሉ ጊዜ ከእስላሞቹና ከፈላሾቹ ባላባቶች መካከል ቀንደኛ ሲነሣ ከኢትዮጵያ ከክርስቲያኑ መንግሥት የመገንጠል ምኞት ያድርበትና ይሸፍታል ። በሸፈተ ቍጥርም ነገሥታቱ ወይም የጦር አለቆች ሠራዊታቸውን ይዘው ሄደው ሽፍትነቱን ለመደምሰስ በሚደረገው ዘመቻ በቀንደኛው መሸፈት የተነሣ በገራገሩና በየዋሁ ባላገር ላይ የሚደርስበት መከራ ከፍ ያለ ነው ። ባላባቱን እንከተልም ቢሉ ደግሞ በቀጥታ በባላባታቸው በኩል የሚሰነዘርባቸው በትር ከዚያ የበለጠ ሊሆን ይችላል ።

የነዚህን የሦስቱን ሃይማኖት የያዙት ወገኖች እንደዛሬ የሃይማኖት ጉዳይ ባል ቀዘቀዘበት በሩቁ ዘመን ያን ጊዜ አብሮ መኖር አብሮ መብላት መዋደድና ያገር ሰው ወገኔ እየተባባለ በመኖር ፈንታ የመናናቁ የጠቡ የውጊያው ውዝግብ ብዙ ነው ። ክርስቲያኑ ከእስላሙ ጋር ቢፋቀር እስላሙ ወይም ፈላሻው ከክርስቲያኑ ጋር ቢውል ቢያድር ፥ በማዕድና በሌላውም ተቀራርቦ ማኅበራዊ ኑሮ ቢፈጽም በየ በኩሉ ወቃሽና ተቆጭ አለበት ፤ ጋብቻማ መቼም የማይከጀል መሆኑ እስከ ጊዜያ ችን ደርሷል ።

ስለዚህ ይኸ ሁሉ በየጊዜው እየተቀሰቀሰ ለመንግሥት ጸጥታና ለማኅበራዊ ኑሮ ችግር መፍጠሩ ስለተሰማቸው የቀድሞዎቹ ነገሥታት ያዘወተሩትን ሕግ በማ ጽደቅ ዓፄ ዮሐንስ ጻድቁ (፲፮፻ - ፲፮፻፸፬ ዓ. ም.) የዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ አባት በኢትዮጵያ ስለሚኖረው የፈረንጅ ዜጋ [illegible]ስላም ስለፈላሻ እንደዚህ ሲሉ ዓዋጅ ነገሩ (1) ።

፩ኛ. ፈረንጆች በተለይ ከዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን ዠምረው የካቶሊክን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ለማስገባት እየተጣጣሩ በዓፄ ሱስንዮስ ዘመን ሁከት ያስነሡት ከሁለት አንዱን እንዲመርጡ ሲሉ «ፈረንጅ አገራችንን ለቆ ወደ አገሩ ይግባ የኛን እምነት ተቀብሎ እንደኛ ተጠምቆ ቀርቦ የሚኖር እንደሆነ ባገራችን ይቀመጥ ይኸን ካልፈለገ ይሂድ»

፪ኛ. እስላምና ፈላሻ ግን ያገር ተወላጅ ከመሆኑ የተነሣ ካገር ይውጣ በማለት ፈንታ "ከክርስቲያኑ እየተለየ ለብቻው መንደሩን ሠርቶ ይቀመጥ" ብለው አወጁ ።

በዚያን ጊዜ ነገሥታቱ ከዚህ የተሻለ መፍትሔ ስለአጡለት እንደዚህ ሦስ ቱም ባለሃይማኖት ዜጋቸው በኑሮው እየተለየ ተቀምጦ ለመንግሥቱ በሰላም እየገ በረ እንዲኖር ለማድረግ ተገድደዋል ። በዚያው በግዛቱ እንደ ገራድ ሐድያ እንደ ይፋት ወላስማ ያለውን እየሾሙ ከእያንዳንዱም እየተጋቡ ኑረዋል ። ዳሩ ግን ይኸው እንደ አሁኑ እንደ ግራኝ ቀንደኛ እስላም ሲነሣ የእስላሙ ወገን ይከተለ ዋል ፤ እንደርሱም ያለ በተነሣ ቍጥር ፈላሾቹ ምንም ሃይማኖታቸው በትክክል ከነ ርሱ ሃይማኖት ጋር ባይገጥም በክርስቲያኖቹ ላይ ያላቸውን ያለፈ ቂም ለመበቀል ከአዲሱ አሸናፊ ጋር ይደረባሉ ። የይሁዲን ሃይማኖት የያዘ በግራኝ መልክ ሆኖ

(1) ታሪክ ነገሥት እዕእላፍ ሰገድ Ignazio Guidi ገጽ 9

ቢመጣ ከዚያ የበለጠ በደስታ ለመቀበል ይኸው እላይ ያልነው ምክንያት እንደሚገፋቸው አይጠረጠርም ።

## ምዕራፍ ፺፫

## የባሕር እምባ ክርስቲያኖችና የፈላሾቹ የቆየ ጠብ — የስሜንና የወገራ ለግራኝ መገበር ። (፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ሚያዝያ - ነሐሴ)

ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው «ሃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው» የሚለው ዘመናዊው ያገር ፍቅርን ዓላማ የያዘው አነጋገር ደህና አድርጎ ባልተሰበከበት በዚያን ዘመን በዘር በቀለም አንድ የሆኑት ሁሉ በሃይማኖት ስለተለያዩ እርስ በርሳቸው ሲተላለቁ ኖረዋል ። ባሁኑ ዘመን ግራኝ አህመድ ያመጣው የጦርነት መከራ የግዛት የበቀል ምኞት ቢጨመርበትም ዋናው የጦርነቱ መሠረት የሃይማኖት ልዩነት ነው ። ከሥሩ ለሕይወት ለመዳኛ ለግብረ ገብነት የተመሠረተው የኦሪት ፣የወንጌል ፣ የቁራን መጻሕፍት መሥራቾቹና ዓላማቸው ከመለያየታቸው የተነሣ ለሕዝብ መተላለቂያ ምክንያት መሆናቸው ያሳዝናል ።

ነገር ግን የበለጠ የሚገርመው በክርስትናም ውስጥ ያሉት በዓለም በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ባገራችን በቅባትና በጸጋ ወይም በካራና በጸጋ የተነሣ መተላለቃቸውን ስንመለከት በማናቸውም ረገድ ሕዝብ ለሰላማዊና ለጤናማ ኑሮ አለመታደሉን እንመለከታለን ። በዚህ ምክንያት ከ፲፩ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ዠምሮ እስከ ፲፫ኛው መቶ ዓ. ም. ድረስ በክርስቲያኖቹና በእስላሞቹ መካከል በኢየሩሳሌምና በኢየሩሳሌም ዙሪያ የተደረገው የመስቀል ጦርነት የተባለው ታሪክ ብዙ ሲሆን የእልቂቱ ቀጥተኛ ምክንያት የሃይማኖት ልዩነት መሆኑ ስውር አይደለም ።

እነሆ በኢትዮጵያም ካፄ ዓምደ ጽዮን ዠምሮ ያላቋረጠው ጦርነት አሁን በግራኝ አህመድ ጊዜ ከዋና የእፍላ ጦርነት ላይ ነው ። ግራኝ አህመድ ከመነሣቱ ቀደም ብሎ በ፲፮ኛው መቶ ዓመት ላይ ከበለው ነገድ አብደላ የሚባለው ከትግሬ ወደ አዳል ተዛውሮ እንደበረከተ ከነዚሁ ውስጥ ከግራኝ ጋር አብረው ዘምተው በቀል ባለበት ትጋት ክርስቲያኑን እንደሚፈጁ የደብረ ሊባኖስ አቃጣይ የበለው ነገድ መሆኑን ፤ አሁንም ግራኝ የደቡቡን ክፍል ከወረረ በኋላ ወደ ትግሬ ግዛት ገብቶ ወረራውን ሲቀጥል የበለው እስላሞች እንደምን እንዳቀፉት ሊከላከሉ የተሰለፉትን የትግሬ ክርስቲያኖች ለማጥፋት መሣሪያ እንደሆኑት አንብበናል ።

በሰሜን በወገራ የሚኖሩት ፈላሾች ሃይማኖታቸው አይሁድ እንጂ እስላሞች ስለአልሆኑ የግራኝን አመጣጥ እንደ መዘጋ እንደ ሐድያ እንደ በለው ሕዝብ በታላቅ ደስታ የተቀበሉት አይመስልም ።

ነገር ግን ባለፈው እንዳመለከትነው በክርስቲያኖቹ ነገሥታትና አገረ ገዥዎች ሥር በሚተዳደሩበት ጊዜ በሃይማኖታቸው ምክንያት ወይም ግብር ከልክለው ሲሸፍቱ ወይም ነጋሚው ደከም ብሎ እነርሱ ኃይል ተሰምቷቸው ለመለየት በሸፈቱ

ቍጥር በተደረገባቸው የመደምሰስ ሥራ ምክንያት ብቻ በክርስቲያኖቹ ላይ ጥላቻና ቂም አድሮባቸው በአሁኑ ሰዓት የግራኝን ወረራ በመደገፍ በክርስቲያኖቹ ላይ የመበቀል ሥራ መሥራታቸውን ዓረብ ፋቂህ የሚያመለክተውን በዚሁ ምዕራፍ ፍጻሜ ላይ እናነባለን ።

ከዚያ በፊት ከፈላሻዩቱ ከዮዲት አነሣሥ በኋላ እላይ እንዳመለከትነው በዚያን ዘመን በሚጠላው አይሁዳዊ ሃይማኖታቸው ምክንያት ብዙ ጊዜ የአይሁድን ሃይማኖት ከዳችሁ ተጠመቁ ቁረቡ ክርስቲያን ሁኑ አንሆንም በመባባል ወይም ሸፍተው ግብር በመከልከል ብዙ ጊዜ በክርስቲያኖቹና በፈለሾቹ መካከል ጦርነት ሆኗል ። በጦርነቱም ጊዜ ምንም እንኳን የፈላሾቹ ቍጥር ያነሰ ቢሆን አገራቸው ስሜን ወገራ ጸለምት ተራራማ ከመሆኑ የተነሣ እነርሱን ለመደምሰስና ለማሳመን የሚሄደው ንጉሥ ወይም የጦር አዝማች ብዙ ጊዜ ይፈጅበት ነበር ።

የወገራ ፈላሾች ሸፍተው ስለነበረ ፲፰ ዓመት በነጋሢነት የገዙት ያፄ ዳዊት ልጅ ንጉሡ ይስሐቅ (፲፬፻፯ - ፲፬፻፳፩ ዓ.ም.) ከሸዋ ወገራ ድረስ ሄደው ከመረባው የእሸር ፈላሾቹ ጋር መዋጋታቸውን ግዕዝኛው ታሪክ ነገሥት ያረጋግጣል (1) ። አንዳንዱ የታሪክ ነገሥት ግልባጭ ቤተ እሹር ያለውን ሌላው ቤተ እጁር ይለዋል ። እጁር ምን ማለት እንደሆነ አይገባኝም ። እሹር ግን በዕብራይስጥ ቋንቋ አይሁዶች አሶርን እሹር ይሉታል (2) ። ምናልባት ለነዚህ ፈላሾች እንደ አባት የተቆጠረ የሶርያ ይሁዲ በኢትዮጵያ ይኖር ይሆናል ። ኤስኮሊ ( Aescoly ) ስለ ፈላሾች እንደ አው. ቍጥር ፲፱፻፵፪ ዓ. ም. ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ደራሲው ጐንደር በነበረበት ሰዓት በጅሮንድ ይስሐቅ የሚባል ፈላሻ የአሪት መጽሐፍ ለመሸጥ መጥቶ እንደተገናኘውና በሌላ አገር ፈላሾች (ይሁዳዎች) መኖራቸውን እንደጠየቀውና እዎን አሉ አሪትንም ያከብራሉ ብሎ እንደመለሰለት ቅዳሜንስ ያከብራሉን ቢለው እንዲያውም በቅዳሜ ቀን ምሳና ራታቸውን እንኳን አያበስሉም ብሎ በመለሰለት ጊዜ ቆቡን አውልቆ «ተመስገን የአብርሃም አምላክ» ብሎ እንደዘመረ ያመለክትና ቆብ ማውለቅ በአይሁድ ሥነ ሥርዓት ክልክል ሲሆን እርሱ እንደ ሶርያ ክርስቲያኖች ክርስቲያንና ይሁዲ በሥነ ሥርዓት እንደሚገናኙ ያመለክታል ። ምናልባት እነዚህ በዓፄ ይስሐቅ ላይ የሸፈቱት ዘራቸውን ከአሶር (ሶርያ) የሚቆጥሩ ይኖርባቸዋል ማለት ነው (3) ።

ይኸው ደራሲ ታሪክ ነገሥት ባጭሩ ጠቅሶ ያለፈውን ሰፋ በማድረግ እነዚሁ ፈላሾች የራሳቸውን መንግሥት በወገራ አቋቁመው ጌዴዎን የሚባለውን አንግሠው ሲተዳደሩ ሳለ ዓፄ ይስሐቅ በ፲፭ኛው መቶ ዓ. ም. ላይ መንግሥታቸውን እንዳፈረሰባቸው ወገራንም ከነርሱ ወስዶ እንደሾመበት ያረጋግጣል (4) ።

(1) ወይስሐቅ ካልዕ ወልዱ ለዳዊት ነግሠ ፲ወ፰ ዓመተ ። ወውእቱ ዓፄ ይስሐቅ ዘሖረ እስከ ወገራ ወጸብዖ ለቤተ እሸር ፈላሻ ዘመረባ . . . . . . ታሪክ ነገሥት ገጽ 52

(2) መጽሐፈ ሰዋስው ወመዝገበ ቃላት . . . . . . . ገጽ 246

(3) Notices sur les Falacha-juifs d'Abissinie- A.Z. Aescoly ገጽ 113 - 114

(4) " " " " " " " " ገጽ 93

ምናልባት መንግሥት ከዛጕዬ ወደ ይኵኖ አምላክ ፣ የመንግሥት መደብ ከላስታ ወደ ሸዋ በዞረበት ሰዓት ሰጭዎቹ ዛጕዬዎች ሥልጣናቸውን በመልቀቅ ተቀባዮቹም ገና ባልደረጁበት በ፲፫ኛው መቶ ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ሸዋ የሚቀመጠው ንጉሥ ከወዲህ በይፋት በኩል ከወላስሞች ጋር በሚዋጋበት ጊዜ መካከል ፈላሾቹ የነፃነት ክፍት ጊዜ ስላገኙ ከመካከላቸው ጌዴዎን የሚባለውን አንግሠው በራሳቸው መሪ ለመተዳደር ሞክረው ይሆናል ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ይስሐቅ ባንድ አገር ሁለት ንጉሥ መኖሩን ስለማይቀበሉ በርሳቸው ውስጥ ነግሦ እንዳይባልም ይህ የንጉሥነት ሥልጣን ከርሳቸው እንዳልመነጨ ስለሚረዱት ሌላ የጦር አለቃ ቢልኩም ተራራ ይዞ ብዙ ቀን የደረጀው የፈላሻ ተዋጊ እንደማይበገር ስለሚያውቁት ራሳቸው ሄደው ጌዴዎንን ወግተው አሳምነዋል ማለት ነው ። ፈላሻ ዘመረባ (የመረባ ፈላሻ) የሚልበት ምክንያት በሰፊው የወገራ አውራጃ ውስጥ መረባ የሚባል ሥፍራ ይኖር ይሆን ?

ቀጥሎም ከዓፄ ይስሐቅ ወዲህ ባፄ በእደ ማርያም ዘመን (፲፬፻፷ - ፲፬፻፸ ዓ. ም.) የጸለምት ፈላሾች አብያተ ክርስቲያናት አቃጥለው ስለነበረ ንጉሡ በእደ ማርያም ማርቆስ የሚባለውን የጦር አለቃቸውን ልከው ከፈላሾቹ ጋር ፯ ዓመት ተዋግቶ በመጨረሻ ማርቆስ አሸንፎ ያቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ በራሳቸው እጅ አሠርቶ የቀሩትንም በውድም በግድም እያስቆረበ ክርስቲያን እንዳደረጋቸው ተጽፏል ።

ከበእደ ማርያም ሞት ወዲህ እስክንድር ወጣት ስለሆኑ እስከ ወገራ እስከ ጸለምት ሄደው አባታቸው በአስገዳጅነት ወደ ክርስትና ያገቧቸውን ፈላሾች በሥፍራው ተገኝተው በመቈጣጠር በክርስትናቸው እንዲጸኑ አላደረጉዋቸውም ። ስለዚህ የርሳቸው ዘመን (፲፬፻፸ - ፲፬፻፹፯ ዓ. ም.) ፲፯ቱ ዓመት ለፈላሾቹ ወደቀድሞ ሃይማኖታቸው ለመመለስ አጋጣሚ ጊዜ ፈጥሮላቸው መመለሳቸውን ፤ የፈሩትም ወደ ፈላሻነት ሳይመለሱ በግዴታ ከቆረቡ በኋላ ቁርባኑ ሥጋውን መልሰው መትፋታቸውን ከርሳቸው በኋላ የነገሡት ብዙ ዘመን አምባ ግሼን በመኖር በዕድሜም በትምህርትም የበሰሉት ወንድማቸው ዓፄ ናዖድ በሰሙ ጊዜ በነዚሁ ፈላሾች ላይ ከፍ ያለ ቅጣት አውርደውባቸዋል (1) ።

ስለዚህ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ፈላሾች በአሁኑ ሰዓት የግራኝ አህመድ ጦር የክርስቲያኑን ያፄ ናዖድን ልጅ ያፄ ልብነ ድንግልን ሠራዊት በየጊዜው አሸንፎ የዚሁ የአሸናፊው ኃይል ወደነርሱ በመጣበት ሰዓት እነዚሁ ፈላሾች እንደ በለው ነገዶች ለግራኝ አህመድ ወረራ መሣሪያ መሆናቸውን የዓረቡ ጸሐፊ ዓረብ ፋቂህ ያረጋገጠውን ወደፊት እናነባለን ።

ባለፈው ያነበብነው የጸለምትን፣ የቢገምድርን ፤ የሠራዬን ሹማምንት በውስጡ አድርጎ ከግራኝ ጋር የተዋጋው ሻውል (በግዕዝ ሳውል) የተሰፋ ኢየሱስ ልጅ

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 80 ። ዣን ባቲስት ኩልቦ ፩ኛ ቮሊዎም ገጽ 51 ። የኢት. ታሪክ ከዓፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 57 ገጽ 283 - 286

ISIC

መሆኑን ታሪከ ነገሥቱም ዓረብ ፋቂህ ተስማምተውበታል ።

ሁለቱም ጸሐፊዎች በራሱ ስም በሻውል ላይ ያባቱን ስም መጨመራቸው ምናልባት ተስፋ ኢየሱስ ከልጁ ከሻውል ደመቅ ያለ ስመ ጥርነት ይኖረው ይሆናል ። ተስፋ ኢየሱስ የሰሜን ገዥ ነበር ። ሰሜንም በዚያን ጊዜ አጠራር አንዳንድ ጊዜ ባሕር እምባ ይባል ነበር ። ምናልባት ባሕር አምባ የደመቀው የከተማ ስም ይሆናል ። አንድ አንድ ጊዜ አውራጃዎች በአውራጃነታቸው ስም በመጠራት ፈንታ በከተማው ስም የሚጠሩበት መንገድ እስከ ጊዜያችን ደርሷል ። ለምሳሌ በዛሬ ጊዜ በኋላ የተጉለትና የቡልጋ አውራጃ ግዛት ተብሎ የተለወጠው በፊት በከተማው የደብረ ብርሃን ግዛት ይባል ነበር ። የየረርና የከረዩም ግዛት የናዝሬት ግዛት እየተባለ መቆየቱን እናስታውሳለን ።

ተስፋ ኢየሱስ የባሕር አምባን (ሰሜንን) ግዛት በያዘበት ሰዓት ግራኝ አህመድ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ከሚያዝያ ዠምሮ እስከ ሰኔ ወር ድረስ አምባ ግሼንን ከቦ የወጋ ጊዜ አምባውን ሲከላከል ሆዱንበመድፍ ባሩድ ተመትቶ መሞቱን በምዕራፍ ፫፺ ላይ አንብበናል ። ከርሱ ሞት በኋላ ንጉሡ ነገሥቱ የሰሜንን (ባሕር አምባን) ግዛት ለልጁ ለሻውል ሰጥተውት ኖሮ አዝማች ሆኖ ሊያዋጋ የቻለው በዚሁም ምክንያት ይሆናል ። ዳሩ ግን በውጊያ ተሸንፎ ወንድሙ ገንዘይ ሲማረክ አዝማች ዮሐንስ ለማምለጥ ከወጣበት ዛፍ ላይ ወድቆ ሲሞት ሻውል ግዛቱ ወደ ሆነው ወደ ተራራማው አገር ወደ ሰሜን፩፩ሂድ ወይም ንጉሡ ወደ አሉበት ሠፈር ይመለስ በትክክል ፍጻሜው አይታወቅም ።

ነገር ግን ወደፊት እንደምናነበው እንደበለው ዘር የሰሜን ፈላሾች በክርስቲያኖቹ ላይ ቂማቸውን ለመበቀል በዚህ ጊዜ መነሣታቸውን ስለሚያውቅ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሂዶ ይሆናል እንጂ የሚገጥመውን ስለሚያውቅ ወደዚያ ወደሰሜን የሚሄድ አይመስልም ። ይሁን እንጂ ከርሱ ጭፍሮች ብዙዎቹ የዚያው የሰሜን ሰዎች ስለ ሆኑ ወደዚያው ወደ ሰሜን ሸሽተው መሄዳቸው የታወቀ ነው ።

ዓረብ ፋቂህ አዝማች ዮሐንስ ከሞተበት ፣ ሻውል ከሸሸበት ፣ ወንድሙ ገንዘይ ከተማረከበት ጦርነት ወዲህ በሰሜን በኩል የሆነውን እንደዚህ ሲል ያመጣዋል «የሰሜን አገር ተራራና ምሽግ የበዛበት በመሆኑ በጣም አስቸጋሪ ነው ። ለፈረስም የሚያስሄድ መንገድ የለም በሀበሻ አገር እንደ ሰሜን አስቸጋሪ የሆነ አገር የለም ።

ስለዚህ ይማም ወደሰሜን የሸሹትን እንከታተል ቢል የበለው ሰዎችና ሹማቸው መሐመድ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ሁሉም ወደ ይማም መጡና ወደሰሜን አትሂድ በዚያ ሂደህ ብዙ ዘመን ብትቆይም ምንም ማድረግ አትችልም ቢሉት ፤ ይህ አገር የአገሩ ሁሉ ራስ ስለሆነ ሳላሰልም አልተወውም ። እርሱም ከሰለመ አገሩ ሁሉ ይሰልማል ብሎ መለሰላቸውና ሚስቱን ለመያዣ በእጠገቡ አስቀርቶ የሻውልን ወንድም ገንዘይን ከምርኮኛነት ነፃ አድርጎ በሰሜን አገረ ገዥ አድርጎ ሾመው ። እርሱም ወደሰሜን ሂዶ አገሩን ማስለም ከዠመረ በኋላ እስላሞቹን ከድቶ ሚስቱን ትቶ ሸሽቶ ወደ ክርስቲያኖቹ ገባ ።

በስሜን ብዙ ምሽግ ያለበት ቀጥ ብሎ የቆመ ረዣዥም ተራራ አለበት ። የየአንዳንዱን ቁመት ተራምዶ እጫፍ ለመድረስ የግማሽ ቀን ጉዞ ይፈጀል ። በላዩም ላይ እርሻና አዝመራ ሞልቶበታል ። በዚህ አገር ከመንገዱ ጥበት የተነሣ አንዱ ሰው በሩን ይዞ ብዙ ጦር ወደ ተራራው እንዳይወጣበት ብቻውን ሊከላከል ይችላል። ይማም አብሳማኑርን ወደ ተራራው ልኮት ሳለ በሰዎቹ (በክርስቲያኖች) ቸልተኛነት የተነሣ ወደ ተራራው ወጥቶ አገሩን ከያዘ በኋላ ወደ ይማም መጣ ። ከባሕር አምባ የተማረኩትንም አርባ የሚሆኑትን ሰዎች አስመጥቶ አንገታቸው እየተቆረጠ ተገደሉ» (1)

በዚህ ዓይነት ዓረብ ፋቂህ በመጨረሻ ጊዜ እንደዠመረው በደካማ አጻጻፍ በስሜን የተደረገውን የጦርነቱን ዝርዝር ሁኔታ ሳይሰጥ የምርኮኞቹን መገደል ብቻ ይጽፋል ።

በዚህም ላይ ግራኝ የአገሩን ሁኔታ ከውስጥ አወቆቹ ከበለው ነገዶች እንደሰማው በጦር የማይበገር መሆኑን ስለተረዳው ያገሩን ሠርዶ በአገሩ አሀያ እንደሚባለው የስሜን ገዥ የነበረውን የሻውልን ወንድም ገንዘይን ሚስቱን ለመያዣ አሰቀርቶ እርሱን ከምርኮኛነቱ ነፃ አድርጎ ሸኆ ላከው ። ሰውዬው ግን ከሚስቱ ፍቅር ይልቅ የሃይማኖቱ በጠቅላላው የወገኑ ፍቅር ስለባሰበት ሹመቱንም ሚስቱንም ትቶ በሽሽት ለግራኝ ወደ አልገበሩት ክርስቲያኖች ምናልባትም ወደ ንጉሡ ሄዶ ተደባልቋል ማለት ነው ። ታሪከ ነገሥቱ ግን ሁኔታውን ሳይዘረዝር መሞቱን ከዚህ በፊት ገልጿል ።

ይኸውም ሆኖ ዓረብ ፋቂህ እንደሚለው በሰዎቹ ቸልተኝነት ከግራኝ የተላከው አብሳማ ኑር ሄዶ ያስገበረው ያንዱን የስሜንን ክፍል እንጂ የክርስቲያኖቹን ኃይል በጦር ደምስሶ በሙሉ ስሜንን እንዳላስገበረ የምንረዳው ከዚሁ ቀጥሎ የፈላሻዎቹን ሁኔታ በማያያዝ ሌላ ጦርነት መደረጉን እንደዚህ ሲል ይቀጥላል ። «በስሜን የሚኖሩት በነርሱ ቋንቋ ፈላሾች የሚባሉ የሀበሻ ይሁዳዎች ናቸው ። አንድ አምላክን ብቻ ያምናሉ ። ነገር ግን ነቢያትም ጻድቃንም የላቸውም እነርሱም የባሕር አምባ ሰዎች (ክርስቲያኖቹ) ከአርባ ዓመት ዠምሮ ባሪያ አድርገዋቸው ለራሳቸው እያሳረሱ ያስገብሩዋቸው ነበር ።

ይማም ሻውልን ካሸነፈ ወዲህ እነዚሁ ፈላሾች ቤት ስለሌላቸው ከተራራው ከየምሽጋቸውና ከየዋሻቸው ውስጥ እየወጡ ተሰብስበው በሚያስደንቅ ሰልፍ ወደ ይማም መጡና በኛና በባሕር አምባ ሰዎች መካከል ከአርባ ዓመት ዠምሮ የቆየ ጠላትነት አለን ። ስለዚህ የተረፉትን እኛ ሄደን ወግተን ደስ በሚያሰኝህ ዓይነት እንገድላቸዋለንና አንተ ዝም ብለህ በሰፈርህ ተቀመጥ ለነርሱ እኛ እንበቃቸዋለን አሉት ።

በዚህ ምክንያት ይማም እነርሱን የሚረዳ ሌላ ጦር ጨመረላቸውና አብረው ወደ ባሕር አምባ ተራራ ወጥተው ሰዎቹን እሥረው ወደ ይማም እሀመድ አመጡ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 455 - 456

ለት ። እርሱም በሙሉ ሰሜን እስኪገብር ድረስ በዚሁ አገር ተቀምጦ የባሕር አም ባን ሰዎች ከየአሉበት ጨርሶ አስወጥቶ አስገደላቸው ። ከዚያ በኋላ ለሰሜን አገር ኡስማን ቤን ጃውሂርን ከርሱም ጋር ፋራቃሃም ኡስማንን ሾመና የሰሜን ሕዝብም በኋላ ከፈላሾቹ ታርቆ በስምምነት ለእስላሞቹ ያርስ ጀመር ። በበኩሉ ወዚር አባ ስም እስላሞቹ በሰሜን ያደረጉትን በሰማ ጊዜ እርሱም በበኩሉ በወገራ ተራራ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ ። ወዚር ሙጋሂድንም ወደ ቤገምድር ላከውና ባገሩ ገብቶ አገሩን እየመታ አሳመነ ። የአገሬውም ተወላጆች ሰላም ለምነው ለእስላሞቹ እያረሱ ግብር እየገበሩ ተቀመጡ» (1) ።

አሁንም ዓረብ ፋቂህ በግራኝ ፊት ፎክረው የሄዱት ፈላሾችና የባሕር አምባ ክርስቲያኖች እንደ'ሸምብራ ኩሬ እንደ አይፈርስ ጦርነት የተዋጉበትን ሁኔታ ላይ ዘረዝር ወይም የግራኝ ጦርና ያገር ተወላጆች ፈላሾች በኅብረት ሲሄዱባቸው ክርስ ቲያኖቹ መከላከል ጥቅም የሌለው መሆኑን አምነው እጃቸውን መስጠታቸውን ሳያወሳ የክርስቲያኖቹን ታሥሮ መምጣት ግራኝ ሰሜን በሙሉ እስኪገብር ድረስ የባሕር አምባን ክርስቲያኖች እያስፈለገ አስወጥቶ ማስገደሉን እነሱም ሲያልቁ ወይም ሲገብሩ በሰሜን ላይ ኡስማን ቤን ጃውሂርንና ፋራቃሃም ኡስማንን መሾ ሙን ብቻ ይናገራል ።

ዓረብ ፋቂህ ቀድሞ በየጦርነቱ ላይ እየተገኘ ባልነበረበት ላይ ምርኮኛን እየ ጠየቀ አንባቢን በሚያጠግብ ሁኔታ የግራኝን የወታደርና የሹማምንት ስም እያ ወሳ ገዳይን ሟችን እየጠቀሰ ጉበዙንና ፈሪውን እየለየ ይጽፍ የነበረውን በአሁኑ ሰዓት ችላ ማለቱ እዚህም ላይ ይታያል ። ጦርነቱ ከተዠመረ ፰ ዓመት ስለሆነው ከዚህ በፊት እንዳልነው ቀድሞ የነበረው ትኩስ መንፈስ እያደር ቀዝቅዞ የኛ ታሪክ ነገሥት እንደሚያደርገው አንዳንዱን ፍሬ ነገር ብቻ እየጠቀሰ ማለፉ በብዙ ቦታ ይታያል ። ያለዚያ ግን በባሕር አምባ ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉ ፈላሾችና እስላሞቹ ባንድነት ሲሄዱባቸው እጃቸውንም በሰላም ቢሰጡ ወደ ግራኝም ቢቀርቡ የሚደር ስባቸውን የሞት አደጋ ስለማይስቱት ሳይዋጉ እንደዚሁ እጃቸውን ሰጥተዋል ማለት አይቻልም ። እጅ መስጠት ቢያምራቸው እስላሞቹና ፈላሾቹ ሳይሄዱባቸው ገና አገረ ገዥቸው ሻውል እንደተሸነፈ ወደ ግራኝ ሊገቡ በቻሉ ነበር ።

ፈላሾቹ ከግራኝ አህመድ ፊት በቀረቡ ጊዜ "በባሕር አምባ ሰዎችና በኛ መካ ከል ከአርባ ዓመት ዠምሮ የቆየ ጠላትነት አለን ያሉትን አንብበናል ። አሁን ግራኝ አህመድ ሰሜንን የሚያስገብርበት ዓመት ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ነው ። ከዚህ ላይ አርባ ዓመትሲቀነስ ፲፬፻፺፯ ዓ. ም. ይሆናል ። ይኸም ዘመን ያዔ ልብነ ድንግል አባት ዓፄ ናዖድ የነገሡበት ዓመተ ምህረት ነው ።

ስለዚህ ባዔ በእደ ማርያም ዘመን በግድ ክርስትና የተነሡት ወደ ፈላሻነት ተመለሱ ለሰው ይምሰል የተቀበሉትንም ቅዱስ ቁርባን መልሰው ይተፉታል የሚሉ ወሬ ንጉሡ ዓፄ ናዖድ የሰሙ ጊዜ እፊታቸው አቅርበው ያስፈጁበት ወደ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 457 – 460

ስሜንም ጦርና አገረ ገዥ ልከው ያጉላሉበት ጊዜ ያው የነገሡበት ዓመት ፲፭፻፲፬ ዓ. ም. መሆኑ ነው ።

ስለዚህ በዚህ ዓይነት ጥቃት የቆዩት ፈላሾች በሃይማኖት ባይመስላቸውም ያጠቃቸውን የክርስቲያን መንግሥት ሊያጠቃ በመጣበት ጊዜ ከርሱ ጋር ተደርበው መሣሪያ ሆነው የጥቃት ብድራቸውን መለሱ ቢባል እምብዛም ሊያስገርም አይችልም ። ስለዚህም በነርሱም ላይ ወቀሳ ለመሰንዘር ያዳግታል ። በዚህ ምክንያት እነርሱ ከተወቀሱ ያጠቁዋቸው ክርስቲያኖች ከወቀሳ አይድኑም ። ነሥታቱ ሊያጠቁዋቸው የቻሉት ፈላሾቹ ከጠቅላላው ከኢትዮጵያዊነት አካል ለመገንጠል ጥፋት ስለአሳዩ እንደሆነ የመገንጠል ስሜት የመጣው በሃይማኖት ልዩነት በልዩነቱ ሰበብ በሚሰነዘር ጥቃትና ንቀት እንደሆነ ጉዳዩ ተጠቃሎ በዛሬው መንፈስ ሲታሰብ ሁሉንም ኃጢአተኞች ወይም ሁሉንም ንጹሐን ያደርጋቸዋል ፣

## ምዕራፍ ፺፩

ግራኝ አህመድ በየአውራጃው ሹማምንቱን በሹመት ከደለደለ በኋላ ደምቢያ የራሱ መቀመጫ እንድትሆን መርጦ እንደተቀመጠባት (፲፭፻፳፰ ዓ. ም.)

ISIC

ዛሬ የቤገምድርና የስሜን ተብሎ ባንድ ጠቅላይ ግዛት የተመደበውን የስሜንን ፣ የወገራን ፣ የጸለምትን ፣ የቤገምድርንና የደምቢያን አውራጃዎች በአስገበረበት በ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ግራኝ አህመድ የኢብራሂም ልጅ ከሥር ከፋኑኤል ጋር በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. በደዋሮ ከተዋጋበት ጊዜ ዠምሮ ያለው ጊዜ ሲታሰብ አሥር ዓመት ይሆናል ።

ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳወሳነው የግራኝ ደንበኛው ጦርነት የሚዠምረው ከራስ ደገልሃን ጋር የተዋጋበት ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ስለሆነ ከዚህ ጊዜ ስንዠምር እስካሁን የ፰ ዓመት ጊዜ አልፏል ማለት ነው ። በነዚህ በስምንት ዓመታት ውስጥ ግራኝ አህመድ ከነጦሩ ያደረገውን የወረራ ተግባር ፣ በግዛት በየተራ በመያዝ ሹም ሽር ያደረገባቸውን አውራጃዎች ባለፉት ምዕራፎች ተመልክተናል ።

ከ፲፭፻፲፱ እስከ ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ደዋሮን ፣ ይፋትን ፣ ሸዋን ፣ ፈጠጋርን ፣ ባሌን ዛሬ አሩሲ ወንጅ የሚባለውን ያን ጊዜ የማያ ሕዝብ የሠፈረበትን ወጅ የሚባለውን እንደዚሁም የዛሬው አዲስ አበባና የአዲስ አበባ ዙሪያ ያዲስ ዓለም ፣ የአምቦና የጅባት ወረዳዎች የጉራጌና የሐድያ አገሮች እስከ ወላሞ ድረስ ያሉት አውራጃዎች በሙሉ ተይዘው በግማሹ የታመነው እስላማዊ ያገር ተወላጅ የቀረውም ከርሱ ጋር የመጣው ሹማምንት እንደ ደረጃው በሹመት ተደልድሎባቸዋል ። ዛሬ በኬንያና በውጋንዳ በሱዳን ጠረፍ አቅራቢያ የሚገኙትን የሲዳሞና የቦረና የወለጋና የጐሬ ወረዳዎች ለጊዜው ቢተርፉም በርቀታቸው የተነሣ ወይም የደረጀ ተከላካይ ጦር የለባቸውም ተብሎ በቸልታ ያመለጡ ወይም በመላላክ የገበሩ በመሆናቸው በጠቅላላው የግራኝና የጦሩ አሳብ ተጠቅሎ ያመ

ራው ግን ንጉሡ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ተከላካይነቱ ወደሚያሠጋው ወደ አማራ ውና ወደ ትግሬው አውራጃዎች ነው ።

ስለዚህ ከ፲፭፻፳፩ እስከ ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ እነሆ ያን ጊዜ ቤተ አምሐራ የሚባለውን የዛሬ ወሎን ያን ጊዜ አንጐት እየተባለ በጠቅላላው የሚጠራውን የሰቆጣን ፤ የላስታን ፤ የኮረምን ፤ የአሸንጌን ወረዳዎች ካሳመነ ወዲህ ወደ ትግሬ አውራጃዎች ተላልፎ ባስገበረበት ጊዜ መካከል በ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. ከመ ዘጋ በጸለምት በወገራ በኩል አልፎ በደንቀዝና በእንፍራዝ በኩል ንጉሡን ሌት ተቀን አሳዶ በደራና በፎገራ ደርሶባቸው ባሕር ዳር ግድም ሊይዛቸው ሲል በፈረስ ለጥቂት አምልጠውት ወደ ጐጃም ከገቡ ወዲህ ተስፋ ቆርጦ ከጐጃም ወሰን ይኸ ውም ከዓባይ ዳር ወደ ሐይቅ (ወሎ) ከዚያ ወደ አክሱም ከአክሱም ወደ ሠራዬ ከዘ ለቀ በኋላ እንደገና ወደ ሺሬ ከሺሬ ወደ ጸለምት ከጸለምት መዘጋ ከመዘጋ ወደ ሰሜንና ወገራ በተመለሰበት ጊዜ ከነሻውልና ከነአዝማች ዮሐንስ ጋር ተዋግቶ በዚህ ክፍል ያለውን ግዛቱን ለማረጋገጥ ችሏል ።

በትግሬ የተነሣው ረሃብና በሽታ ሰውን የፈጀበት ጊዜ ወደ ደምቢያ ከመም ጣቱ በፊት ሹም ሽር አድርጎ ፤

ሠራዬን ለተስፋዊ

ሐማሴንን ለዘርዓ ሠናይ ISIC

ባሕር ነጋሽነትን ለአፍራ

የድሆኖን ወደብ (የአርኪቆን ወደብና አካባቢውን) ቀደም ብሎ ለተከታዩ ለሽሪፍ ኑር ከሰጠ በኋላ እንደገና ላገሩ ባላባት ለሱልጣን አህመድ ቤን ኢስማኤል መስጠቱን ባለፈው አንብበናል ።

አሁን ደግሞ ባለፈው ምዕራፍ እንደተገነዘብነው ከአክሱም በሺሬ በኩል አድርጎ ፪ኛ ሲመጣ በጸለምት ፤ በወገራ ፤ በሰሜን ፤ በቤገምድር የተከላከሉትን የክ ርስቲያን ሹማምንት በመፍጀት ወረዳውን ሁሉ ግራና ቀኝ ጦር እየላከ በመውጋት አጣርቶ ካሳመነ በኋላ በተያዘውና በገበረው አገር ላይ ሹም ሽር አድርጎ ደምቢያን ግን የራሱ መቀመጫ እንድትሆን መረጣት ። የመረጣትም በፊተኛው ንጉሡን ባሳ ደደበት ወቅት ያገሪቱን ልምላሜ በማየት ወዷት ስለነበረ ነው ። ስለዚህ ደምቢያን ለራሱ ከመደበ በኋላ በቀሩት ወረዳዎች ከዚህ እንደሚከተለው ሹም ሽር አደረገ ።

፩ኛ. ወገራን ለገራድ ሳብር ዲን (ሰበርዲን) ።

፪ኛ. ደራን ለፈራቃሃም አሊ ሲሰጥ በርሱ ውስጥ ፈራቃሃም ሱልጣን አዲል ሽምሱ ተክላይ ተደልድለዋል ። ደራ ማለት ዛሬ በደብረ ታቦር አውራጃ ግዛት ውስጥ የወረዳ ግዛት ሆኖ በውስጡ ላይ ደራ ፣ ታች ደራ ፤ ላይ አፈር ዋናት ታች አፈር ዋናት ያሉበት ነው ። እርሱም ከወገራ ንጉሡን ለመማረክ እያባ ረረ ያለፈበት የፎገራና በባሕር ዳር አጠገብ የሚገኘው ለምለም አገር ነው ።

፫ኛ. ከቤገምድር እስከ ወፍላ ድረስ ያለውን ታላቅ ያማራ አገር ሰቆጣንና ዋግን ጭምር ለስመ ጥሩው ተዋጊ ለቀጭኑ አቡበከር ሲሰጥ በርሱ ውስጥ የበ ለው ነገድ ሹማምንት እነሹም መሐመድ እነሹም ሹከር ተደልድለዋል ።

ዓረብ ፋቂህ ይኸን ሹም ሽር በተረከበት ላይ እያንዳንዱ ሹም በተሾመበት አገር መስጊድና ከተማ መሥራቱን ፣ የአገሬው ሕዝብ የእስላሞቹ ገባርና አራሽ መሆኑን እየጨመረ ይገልጻል ። ግራኝ አህመድ በነዚህ በትግሬና በሐማሴን በወራና በቤጌምድር በደራና እስከ ወፍላ ድረስ በሚገኘው የአማራ የየጁና የላስታ ግዛት ላይ ሹም ሽር ሲያደርግበት ጐጃምንና አገው ምድርን የዘለለው ገና በሙሉ ያልተገዛ አገርና ንጉሡም ከዓባይ ዳር ከመግረክ ተርፈው የሂዱበት አገር በመሆኑ ነው ። ነገር ግን ግራኝ ደምቢያ በነበረበት ባሁኑ ጊዜ እርሱ ከደምቢያ ገራድ ሻሙን (ስምዖን) የሚባለው የጦር አለቃ ከግድም መጥተው በጐጃም መገናኘታቸውን የዓረቡ ጸሐፊ ይጠቅሳል ።

ታሪከ ነገሥቱ ሹም ሽሩንም የደምቢያን መመረጥም ባያነሣም የነሻውልን መሸነፍ የነአዝማች ዮሐንስን ተዋግቶ መሞት ካወሳበት ቀጥሎ «ሻውል ተዋግቶ ተሸነፈ ። አዝማች ዮሐንስ ገንዛይና ቡሳ ሞቱ ግራኝ ስሜንንና ደምቢያን ቤገምድርን ገዝቶ በዚያው ተቀመጠ» ያለውን እናስታውሳለን ።

የዓረቡ ጸሐፊ በዚሁ መጽሐፉ ላይ የቀረውን አውራጃ ሁሉ ለየሹማምንቱ አከፋፍሎ ደምቢያን ለራሱ መርጦ እንደ ጉልት ያስቀረበትን ሁኔታ እንደዚህ ሲል በራሱ አነጋገር ገልጾታል ። «ይማም ከወገራ ወደ ደምቢያ ሄደ ። ይቺም አገር መልካም ነገር የመ[illegible]ናት ። እርሷንም የሚመስል በአበሻ አገር የለም ። ድርቀት አታውቅም ። ከአገሩ ፍሬያማነት (ለምለምነት) የተነሣ በደምቢያ እንደበሬ የወፋፈሩ ፈረሶች የሚውሉበትና የወርቅ ገበያ አለ ። አገሪቱን ብዙ ሌሎች አገሮች ይየሰኑዋታል ። ከነዚሁ ውስጥ ወርቅ የሚመጣበት የኑብያዎች አገር ነው ። በዚህ ምክንያት ይማም ይቺን አገር የራሱ ከተማ እንድትሆን መረጣትና በፍጹም ነፃ አድርጎ አገሬው ለእስላሞቹ አራሽ ከሆነ በኋላ መስጊዶች አሠራባት ። አውራጃዋንም እስከ መጨረሻው ፈረሰኛ ድረስ ለጓደኞቹ አከፋፍሎ ሰጣቸው ። ከሐምጃን ጋር የሚዋሰነውን የተከን ግዛት ለወዚር አባስ ሰጠውና እስላሞቹ ሁሉ ዕረፍትን ያጣጥሙ ዠመር» (1) ...... ።

በኢትዮጵያ ምዕራብና ደቡብ ክፍል የሚገኙ አውራጃዎች አልፎ አልፎ ወንዛ ወንዞችና ሐይቆች በሐይቆቹ ውስጥ ለምለም ዕፀዋትና ሳር የለበሱት ደሴቶች አሉ ። በአካባቢያቸው የሚገኙት ለምለም የሞላባቸው ያሩሲና የባሌ የሻሸመኔ የዟይ የወላሞ የገሙጐፋ (አርባ ምንጭ) ወረዳዎች ከወዲህ ደግሞ የጊቤን ወንዝ ተሻግሮ በጅማ በአጋሮ በሊሙ በጌራ በጃንጀሮ እስከ ጐሬ ድረስ ያለው የወለጋ አገር ሁሉ ለሰውም ለእንስሳም ኑሮ የተመቸ በለምለምነቱ አስደናቂ መሆኑ አያጠራጥርም ። የሸዋና የወሎ የትግሬ አውራጃዎች አልፎ አልፎ እንደዚሁ ለምለምነት ባያጡም በግማሹ ገደላ ገደል በግማሹ ድርቀት ስለሚፈራረቅበት የነዚህን ያህል አያመችም ።

በኢትዮጵያ ምዕራብ ደግሞ ከሸዋ የዓባይን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ ከደጀን

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 460 - 462 ። ሐምጃን አምሐጀር ይሆን ባሴት ሬኔ ተከን በአትባራ በኩል በተከዜ የሚዋሰን የከሰላን አካባቢ ሁሉ አድርገውታል ። ማስታወሻ ቊ. 2 ገጽ 461 ። ቊ. 1 ገጽ 462

ዝምሮ በደብረ ማርቆስ በደምበጫ በሜጫ በአገው ምድር አልፎ እስከ አቸፈር በጣና አካባቢ ያለው የዘጌ ምድር ሁሉ እንደዚሁም ከላይ በሺሬ በኩል ወገራን ፤ ቤገምድርን አልፎ ከዛሬው ከጐንደር ከተማ ጣቁሳን ጭልጋን አይከልን መተማን ወደቀኝ በለሳን ደብረ ታቦርን እስቴን ደንቀዝንና እንፍራዝን ፎገራንና ደራን ወደ ግራ እየተዉ ወደ ደምቢያ ወረዳ ገብቶ በቀጥታ የቆላ ድባን ከተማና ወረዳ አልፎ ከጣና ሐይቅ ዳርቻ ጕርጕራና የሱስንዮስ ቤተ መንግሥት ፍራሽ ወዳለበት ጉብታ (1) ። ሲደረስ የዚህ አገር ዙሪያ ገቡ ለምለም ፊት ለፊት የሚታየው የጣና ሐይቅ ከሐይቁ ውስጥ ክረምትና በጋ የልምላሜ መልካቸውን የማይለውጠው በያለበት ተበታትነው የሚታዩት የናርጋ ሥላሴ የገሊላ ማርያም የዳጋ እስጢፋኖስ የደቅ ክብራን ገብርኤል ሌሎቹም ገዳማት ያሉባቸው ደሴቶች ባይን ታይተው አይጠገቡም ።

መቼም በአዳል በሱማሌ በረሃና ድርቅ በሚያጠቃው አውራጃ ተወልደው ያደጉት እነዚህ የአዳልና የሱማሌ ተወላጆች ለነርሱ እርዳታ ከበረሃማውና ከአሸዋማው አገር የመጡት ጥርቅም ዓረቦች በነዚህ በስምንት ዓመታት ውስጥ ከበረሃማው አገራቸው ወደ ለምለሚቱ ኢትዮጵያ ገብተው ከአውራጃ ወደ አውራጃ እየተዘዋወሩ በአሸናፊነት ሲገቡ የቤተ መንግሥቱንና የቤተ ክህነቱን የደለበ ሀብት እየዘረፉ ሲከፋፈሉ ነገሩ እንደሚደንቃቸው አሁንም የዚህን የለምለም አገር ትክለኛ ባለቤቶች አጥፍተው እነርሱ የበረሃ አገር ተወላጆች የሆኑት ባለቤት ሆነው በተድላ በደስታ መቀመጣቸው ሳይገርማቸው አይቀርም ። ይኸም ተድላ ደስታ ይኸም የለምለም አገር ባለቤትነት ዘላቂ ይሁን ወይም ጊዜያዊ መሆኑን ከመካከላቸው የሚጠራጠር እንዳለ አይታወቅም ።

ISIC

የፎገራንና የደምቢያን የአገውን ወረዳዎች በተለይም በጣና ሐይቅ ዙሪያ በዘጌ የሚገኘውን ቀበሌ የጐበኙ የውጭ አገር ተወላጆች ሁሉ በሐይቁ ውስጥ ተንጣሎ የተኛውን ንጹሕ ውኃ የደሴቶቹንና በየጠረፉ ዳር ያሉትን ለምለም ሣርና ልዩ ልዩ ዕፀዋት የተጐናጸፉትን ወረዳዎች ያዩ «የምድር ገነት» ነው እያሉ ጽፈዋል ።

በዚህ ምክንያት ምንም እንኳን ባገሩ ርቀት ወይም የዓይነተኛ ጠላቱን የንጉሡን እንቅስቃሴ ለመቈጣጠር ሲል ወደ ሰሜን በማቅናት የደቡቡን ክፍል እንደርባ ምንጭን ለመጐብኘት ጊዜ ባያገኝ እስካሁን ከአውራጃ ወደ አውራጃ እየተዘዋወረ ካየው ሁሉ ለግራኝ አህመድ ደምቢያ በልጦበታል ። ለውጊያ ምቹ ሥፍራ በመምረጥ የታወቀው ግራኝ ለመኖሪያም ከሁሉ የተሻለውን ሥፍራ ለይቶ የመምረጥ ዕድል አለው ማለት ነው ።

በትግሬ አገር ረሃብና በሽታ የአስቸገራቸው ጊዜ ማናቸውንም በራሱ ሥልጣን መወሰን ሲችል እንደ መልካም የዴሞክራት መሪ «የደረሰብንን ዓይታችኋል እንግዲህ ወደየትኛው አውራጃ ብንሄድና ብንቀመጥ እንደሚሻል ንገሩኝ» ብሎ

(1) የሱስንዮስ ቤተ መንግሥት እየተባለ የሚጠራው ኢየሱሳውያኑ እነፓኤዝ ያሠሩት ካቶሊካዊ ቤተ መቅደስ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን የካቶሊክን ሃይማኖት የተቀበሉት ሱስንዮስ ከዚያው ጐን ቤተ መንግሥት አያጡም ።

የበታች ሹማምንቱን በጠየቀ ጊዜ ወደ ደምቢያ ወይም ወደ ፎገራ አለዚያም ወደ ቤገምድር እንሂድ ብሎ አሳብ ያቀረበለት የለም ። በበረኸኞቹ እስላሞች ፊት በኢትዮጵያ በየአውራጃው ያዩት ሁሉም ለምለም ሆኖባቸው አንዱን ከሌላው ለማበላጥ ግራ ገብቷቸው እንደሆነ አይታወቅም ።

ስለዚህ የሚመርጡት ቢያጡ «መወሰንና ማዘዝ ያንተ በሂድህበት መከተል የኛ ፈንታ ነው» ስላሉት የጥያቄውም የመልሱም ጌታ እርሱ ሆና ደምቢያን መርጦ ወደዚሁ ወረዳ መጥቶ አገሪቱን ከነጭፍሮቹ ተከፋፍሎ ተቀመጠባት ።

ይሁን እንጂ ግራኝ በዚች በወደዳትና ለኑሮ በመረጣት የደምቢያ ወረዳ ዕድሜውን በተድላና በደስታ ሊፈጽምባት አልቻለም ። በዚያን ጊዜም ቢሆን ዓፄ ልብነ ድንግል በሕይወት እስካሉ ድረስ ሙሉ ዕረፍት አላገኘም ። እርሳቸውም በመከራ መካከል ቢሞቱ ወራሴ መንግሥታቸው ገላውዴዎስ ከነገሡ በኋላ ለዕርዳታ የመጡት ፖርቱጊዞች ተባብረው ሰፊ ዓላማ የነበረውን የግራኝ አህመድን ሕይወት ባጭሩ ሲቀጩት ወደፊት በየምዕራፉ ይነበባል ። ወራሪ ሁሉ ለጊዜው ባገኘው አቅም ከአንድ የከንውን ደረጃ ላይ ሲደርስ በኃይልና በጉልበት ያገኘውን እንደ ሕጋዊ ወይም እንደዘለቄታ የሀብት ውርስ በመቁጠር ይደሰታል ። ነዋሪ ጥላንም ማዘጋጀት ይጀምራል ። ነገር ግን በሚቀጥለው ጊዜ ያልታሰበ ሁኔታ እየተፈጠረ ነገሩ ይገ[illegible]ጣል ። የኢጣልያና የግራኝ ወረራ ይመሳሰላል እንዳልነው የግራኝ አህመድና የቤኒቶ ሙሶሊኒ ምኞታቸው አነሣሳቸውና አወዳደቃቸው ተመሳሳይ ነው ። በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ላለችው ኢትዮጵያ በግራኝ ላይ የፖርቱጊዞች እርዳታ እንደተገኘ ፤ በ፳ኛው ዓመት ላለችው ኢትዮጵያ ነፃነት ደግሞ የእንግሊዞች እርዳታ ምክንያት ሆኖ የሁለቱም ዲክታተሮች ምኞትና ዓላማ እየወደቀ የወደቀችው ኢትዮጵያ ተመልሳ በእግሯ የመቆም ዕድል አገኘች ።

## ምዕራፍ ፺፰

### በጣና ሐይቅ ስላሉት ደሴቶችና በየደሴቱ ላይ ስላሉት ገዳማት - ስለ ደብረ ገሊላ መበዝበዝ (፲፰፻፰፱ ዓ. ም. ) - ስለ ዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ መቋረጥ

ዓረብ ፋቂህ የግራኝ አህመድን ደምቢያን ለመቀመጫው መምረጥና ተደላድሎ በዚች ለምለም አገር መቀመጡን ከተማ እየከተመ ቤትና መስጊድ ማሠራቱን ከተረከ በኋላ በጣና የደብረ ገሊላን መበዝበዝ ያስከትላል ። ታሪክ ነገሥቱ ግን ምንም እንኳን ዝርዝር ታሪክ ቢነፍገን ባሁኑ ጊዜ የገላቢጦሽ ዓረብ ፋቂህ ያላወሳውን ባጫጭሩ እያመለከተ በደምቢያ ምርጫና በገሊላ ብዝበዛ መካከል ብዙ ታሪካዊ የጦርነት ሥራ እንደተፈጸመ ምልክቱን ያሳያል ። ይኸውም ማለት ግራኝ በሚያዝያ ወር በ፲፰፻፰፯ ዓ. ም. ከነሻውል ጋር በጸለምትና በወገራ አካባቢ ተዋግቶ ከአሸነፈ በኋላ ስሜንንም እየወጋ ያሳመነው በዚሁ በ፲፰፻፰፯ ዓ. ም. መጨረሻ ላይ ነው ። ደምቢያ ደርሶ ተቀመጠ የሚለውም በዚሁ ዓመት ነው ። ከዚህ አያይዞ

ታሪከ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፳፫ኛው ዓመት (፲፭፻፳፫ ዓ. ም.) ግራኝ ወደ ጐጃም ተሻግሮ ብዙ ሰው መግደሉን ከዚያ ወደ ሠራዌ ሄዶ የሠራዌን ሕዝብ እንደፈጃቸው ፤ አምሐ የሚባል ክርስቲያን እስላሙን ፈራቃሃምን እንደ ገደለ ፤ በበኩሉ ግራኝ ደግሞ ወሰና የሚባለውን በመስከረም ፳፩ ቀን በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. ከገደለ በኋላ በዚሁ ዓመት በጣና የገሊላን ገዳም መበዝበዙን ያስከትላል ። ሌላ ደግሞ በአማርኛ ተጽፎ የሚገኝ ባንድ ቦታ ላይ «በሚያዝያ ፳፱ ቀን ሻውል ድል ሆነ አዝማች ዮሐንስና ገንዘ ልዑል ሞቱ ፤ ያፄ ልብነ ድንግል አሽከሮች አለቁ ግራኝ ቤገምድርን ገዛት ፤ የንጉሡ ዓመተ መንግሥቱ ፳፯ ዓመት ሆነ ግራኝ ጐጃም ሄደና መርጡለ ማርያምን ፤ ደብረ ዘይትን ፤ ናዝሬትን ፤ ቀራንዮን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ» ብሎ ወደ ገሊላ ብዝበዛ ይሻገራል (1) ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የመዠመሪያዎቹን የጦርነት ዘመናት (፲፭፻፲፱-፲፭፻፴፬ ዓ. ም.) የደዋሮውን የአይፈርሱን የሽምብራ ኩሬውን የባሌውን የዝሆን ዱሩን የዋሰሉን ጦርነት ሁሉ የሚያጠግብ ዝርዝር እየጨመረ በጥንቃቄና በግለት ይጽፍ የነበረው ዓረብ ፋቂህ ከ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. ወዲህ በአጻጻፉ መቀዝቀዝ አንዳንዱን ታሪክ መቁረጥ ወይም የፊቱን ወደኋላ እያደረገ መጻፍ የዠመረውን አሁን እየባሰበት ሄዶ እንዲያውም የ፲፭፻፳፰ - ፲፭፻፴፱ን ዓ. ም. ሙሉውን ታሪክ እየቀነጨበ ብቻ አልፎ በግንቦት ወር በ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. የተደረገውን የገሊላን ገዳም ብዝበዛ ብቻ ሰፋ አድርጎ ይተርካል ።

ስለዚህ ባለፈው ስለደምቢያ ለምለምነት ስለጣና ባሕር እንደተመለከትን አሁን ደግሞ በሐይቁ ውስጥ ስለሚገኙት ገዳማትና ስለገሊላ ገዳም መዘረፍ እንመለከታለን ።

በገርዖግራፊው ላይ እንደምንመለከተው የጣና ባሕር ከወደ ሰሜን የደምቢያ ወረዳ የቆላ ድባ ከዚያ ዝቅ ብሎ በሐይቁ ዳር የጎርጐራ ከተማ ከምዕራብ ወገን ከላይ ጣቁሳ ከታች ከምዕራብ ደቡብ አገው ምድር ወደ ሐይቁ ጠጋ ብሎ አቸፈር ይዋሰነዋል ። ከምሥራቅ በኩል እምፍራዝ ቃሮዳና ፎገራ በምሥራቅና በደቡብ መካከል ደራ በደቡብ የዓባይ ወንዝ መፍለቂያና መንዝ የሚዠምርበት የባሕር ዳር ከተማ ይገኛል ።

እንደጣና ሰፊና ደሴቶች የሞሉበት ሌላ ሐይቅ በኢትዮጵያ አይገኝም ። መርከቡ ከሚነሣበት ከጐርጐራ ዠምሮ እስከሚያርፍበት እስከ ባሕር ዳር ከተማ ድረስ ርዝመቱ ፹፫ ኪሎ ሜትር መሆኑን የናቪጋና ጣና መርከብ ሠራተኛ ያጫወተኝ ልክ ሊሆን ይችላል ።

ስለጣና ሐይቅ ስለደሴቶቹ በደሴቶቹ ላይ ስለሚገኙት ገዳማት ብዙ የውጭ

(1) መጽሐፈ ታሪክ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ቍጥር 200 - ግዕዙ ገንዛይ ያለውን ገንዘ ልዑል ብሎ ታል ። ግዕዝኛው «ወበ፳ወ፰ ዓመተ መንግሥቱ ጓደወ ምድረ ጐጃም ወቀተለ ብዙኃነ ወወረደ ሠራዌ ወፈጸሞሙ ወቀተሎ አምኃ ለፈራሻም እስላም ። ወበ፳ወ፱ ዓመተ መንግሥቱ ቀተሎ ለወሰና አመ ፳ወ፩ ለመስከረም ። ወበውእቱ ዓመት ውእየት ገሊላ ማእከለ ደሴት» ይላል ። ባሴት ረኔ ያሳተመው ታሪከ ነገሥት ገጽ 329 ።

አገር ጸሐፊዎች አድናቆት ከመጨመር ጋር በየቋንቋቸው ጽፈዋል ። ፈረና
ኒዩ የሚባሉ ሁለት ፈረንሳዮች «እንደ ጣና ሐይቅና እንደ አካባቢው አስደ
ነገር የለም ። ጸጥ ያለው ውኃ ቀለሙ ከሰማይ ቀለም ጋር እየተፈራረቀ ጉድፍ
ንካው መስተዋት ይመስላል» ብለዋል (1) ። ለጃን የሚባለው ባዬ ቴዎድ
ዘመን የፈረንሳዊ ቆንስል የነበረው «. . . . . . እነከብራን ፣ እነምጽራሐ ያሉ
ደሴቶች በሩቅ መሬት ላይ ሆኖ ሲታዩ ጨለም ያለ ልምላሜ የለበሱና የሚዋኙ ሐ
ወት ያላቸው ቅርጫቶች ይመስላሉ ፣ ቀረብ ብለው ሲመለከቷቸው ልምላሜ
ቸው የበዛ ዕቅፍ አበባ ሆነው በውስጣቸው በሚገኘው ቋጥኝ ላይ የተከበሩትን ገ
ማት እንዳቀፉ ሆነው ይገኛሉ . . . . . » ብሏል (2) ።

በነዚህ ደሴቶች ውስጥ ያሉት የገዳማት ዝርዝር ከሥፍራው በመገኘት ያጠረ
ቀምሁት ግማሹንም የጐበኘሁት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

፩. ደብረ ገሊላ (አሁን ግራኝ የበዘበዘው) ቀድሞ ባዬ ዓምደ ጽዮን ዘመን በጋብቻ ምክንያት ከእጨጌ ፊልጶስ ጋር ጠብ የተነሣ ጊዜ አባ እንድርያስ የተሰደዱ በት ።

፪. ናርጋ ሥላሴ ኢያሱ ብርሃን ሰገድና እናትዮዋ ንግሥት ምንትዋብ ያሠሩት ።

፫. ዳጋ እስጢፋኖስ ባምደ ጽዮን ጊዜ የተተከለ የብዙ ነገሥታት ዐፅም ያረፈ በት ነው ። ከነዚሁም በታሪክ የታወቁት ቀዳማዊ ዳዊት ከ፲፫፻፸፬ እስከ ፲፬፻፭ ዓ. ም. ፴፩ ዓመት ገዝተው የሞቱት (3) የዓፄ ዳዊት አራተኛ ልጃቸው ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከ፲፬፻፳፮ እስከ ፲፬፻፷ ዓ. ም. ፴፬ ዓመት ገዝተው የሞቱት፤ ከነዚህም ጋር ያፄ ሱስንዮስና የልጃቸው ያፄ ፋሲል ዐፅም ይገኝበታል ። ያፄ ሱስንዮስና የፋሲል መቃብር እንደ ሞቱ ታሪከ ነገሥታቸው ተቀበሩ የሚለው በአዘዞ ተክለ ሃይማኖት ነው ። ነገር ግን የዘርዓ ያዕቆብ ዓጽም ፴ ዓመት ካለፈው በኋላ ባፄ ናዖድ ጊዜ ከነበረበት ወደ ዳጋ ደሴት ሄዶ እንዳረፈ የሱስንዮስና የፋሲልም ዓጽም በልጆቻቸው ጊዜ ከአዘዞ ወደ ዳጋ ደሴት ተዛ ውሮ ተቀምጦ ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ለነዚህ ነገሥታት ዐፅም የኢየሩሳሌም ድርጅት ለየአንዳንዳቸው ባሠራው ሳጥን ውስጥ እንደተቀመጠ በፊት ለፊቱ ባለው መስተዋት ይታያል ።

፬. ጣና ቂርቆስ ፤

፭. ደቅ እስጢፋኖስ እንደ ምጽራሐ የግዞተኛ መቀመጫ ፤

፮. ምጥሊ ፋሲለደስ ፤


፯. ሬማ መድኃኔ ዓለም ፤

፰. እንጦስ መድኃኔ ዓለም

፱. ማንደ ማርያም ፤

(1) Voyage en Abyssinie 2 Vol. ገጽ 257 - 258
(2) Voyage en Abyssinie et autour du monde ገጽ 267 ። ዓረብ ፋቂሀ በረኔ ባሴት ትርጉም ውስጥ የማስታወሻ ቍ. 1 ገጽ 462 ቍ. 1 ገጽ 463
(3) የኢት. ታሪክ ከይሁኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ገጽ 115

# የጣና ሐይቅና ደሴቶቿ ከአብያተ ክርስቲያናቱ ጋር




፩ ገሊላ ማርያም
፪ ናርጋ ሥላሴ
፫ ዳጋ እስጢፋኖስ
፬ ጣና ቂርቆስ
፭ ደቅ እስጢፋኖስ
፮ ምጥሊ ፋሲለደስ
፯ ሬማ መድኃኔ ዓለም
፰ እንጦስ መድኃኔ ዓለም
፱ ማጸ ማርያም
፲ ቤት መንዞ መድኃኔ ዓለም
፲፩ ክብራን ገብርኤል
፲፪ ምጽራሐ
፲፫ ብርጊዳ ማርያምና እግዚአብሔር አብ
፲፬ ደብሊ ማርያም

አገር ጸሐፊዎች አድናቆት ከመጨመር ጋር በየቋንቋቸው ጽፈዋል ። ፈሬና ጋሊኒዬ የሚባሉ ሁለት ፈረንሳዮች «እንደ ጣና ሐይቅና እንደ አካባቢው አስደናቂ ነገር የለም ። ጸጥ ያለው ውኃ ቀለሙ ከሰማይ ቀለም ጋር እየተፈራረቀ ጉድፍ ያል ነካው መስተዋት ይመስላል» ብለዋል (1) ። ለዠን የሚባለው ባዬ ቴዎድሮስ ዘመን የፈረንሳዊ ቆንስል የነበረው «. . . . . . እነክብራን ፤ እነምጽራሐ ያሉበት ደሴቶች በሩቅ መሬት ላይ ሆኖ ሲታዩ ጨለም ያለ ልምላሜ የለበሱና የሚዋኙ ሕይወት ያላቸው ቅርጫቶች ይመስላሉ ፤ ቀረብ ብለው ሲመለከቱዋቸው ልምላሚያቸው የበዛ ዕቅፍ አበባ ሆነው በውስጣቸው በሚገኘው ቋጥኝ ላይ የተከበሩትን ገዳማት እንዳቀፉ ሆነው ይገኛሉ . . . . . » ብሏል (2) ።

በነዚህ ደሴቶች ውስጥ ያሉት የገዳማት ዝርዝር ከሥፍራው በመገኘት ያጠራቀምሁት ግማሹንም የጐበኘሁት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

፩. ደብረ ገሊላ (አሁን ግራኝ የበዘበዘው) ቀድሞ ባዬ ዓምደ ጽዮን ዘመን በኃብቻ ምክንያት ከእጨጌ ፊልጶስ ጋር ጠብ የተነሣ ጊዜ አባ እንድርያስ የተሰደዱበት ።

፪. ናርጋ ሥላሴ ኢያሱ ብርሃን ሰገድና እናትዮዋ ንግሥት ምንትዋብ ያሠሩት ።

፫. ዳጋ እስጢፋኖስ ባምደ ጽዮን ጊዜ የተተከለ የብዙ ነገሥታት ዐፅም ያረፈበት ነው ። ከነዚሁም በታሪክ የታወቁት ቀዳማዊ ዳዊት ከ፲፫፻፸፭ እስከ ፲፬፻፬ ዓ. ም. ፳፱ ዓመት ገዝተው የሞቱት (3) የዓፄ ዳዊት አራተኛ ልጃቸው ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከ፲፬፻፳፮ እስከ ፲፬፻፷ ዓ. ም. ፴፬ ዓመት ገዝተው የሞቱት። ከነዚህም ጋር ያፄ ሱስንዮስና የልጃቸው ያፄ ፋሲል ዐፅም ይገኝበታል ። ያፄ ሱስንዮስና የፋሲል መቃብር እንደ ሞቱ ታሪክ ነገሥታቸው ተቀበሩ የሚለው በአዘዞ ተክለ ሃይማኖት ነው ። ነገር ግን የዘርዓ ያዕቆብ ዓጽም ፴ ዓመት ካለፈው በኋላ ባዬ ናዖድ ጊዜ ከነበረበት ወደ ዳጋ ደሴት ሄዶ እንዳረፈ የሱስንዮስና የፋሲልም ዓጽም በልጆቻቸው ጊዜ ከአዘዞ ወደ ዳጋ ደሴት ተዛውሮ ተቀምጦ ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ለነዚህ ነገሥታት ዐፅም የኢየሩሳሌም ድርጅት ለየአንዳንዳቸው ባሠራው ሳጥን ውስጥ እንደተቀመጠ በፊት ለፊቱ ባለው መስተዋት ይታያል ።

፬. ጣና ቂርቆስ ፤

፭. ደቅ እስጢፋኖስ እንደ ምጽራሐ የግዞተኛ መቀመጫ ፤

፮. ምጥሊ ፋሲለደስ ፤

፯. ሬማ መድኃኔ ዓለም ፤

፰. እንጦስ መድኃኔ ዓለም


፱. ማዶ ማርያም ፤

(1) Voyage en Abyssinie 2 Vol. ገጽ 257 - 258

(2) Voyage en Abyssinie et autour du monde ገጽ 267 ። ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ትርጉም ውስጥ የማስታወሻ ቍ. 1 ገጽ 462 ቍ. 1 ገጽ 463

(3) የኢት. ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ገጽ 115

## የጣና ሐይቅና ደሴቶቿ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር




፩ ገሊላ ማርያም

፪ ናርጋ ሥላሴ

፫ ዳጋ እስጢፋኖስ

፬ ጣና ቂርቆስ

፭ ደቅ እስጢፋኖስ

፮ ምጥሊ ፋሲለደስ

፯ ሬማ መድኃኔ ዓለም

፰ ኢንጦስ መድኃኔ ዓለም

፱ ዑዳ ማርያም

፲ ቤት መንዞ መድኃኔ ዓለም

፲፩ ክብራን ገብርኤል

፲፪ ምጽራሐ

፲፫ ብርጊዳ ማርያምና እግዚአብሔር አብ

፲፬ ደብረ ማርያም

፲. ቤት መንዞ (ጨቅላ ማንዞ) መድኃኔ ዓለም አድያም ሰገድ ኢያሱ የተገደሉበት ፤

፲፩. ክብራን ገብርኤል ባምደ ጽዮን ጊዜ የተተከለና በእጨጌ ፊልጶስ አመንኳሽነት አባ ዘዮሐንስ የገደሙት ፤

፲፪. ምጽራሐ ጻድቁ ዮሐንስና ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል የተቀበሩበት ፤

፲፫ እግዚአብሔር አብ

፲፬. ደብረ ማርያም

የደሴቶቹ ቍጥር እስከ ፴ ስለሚደርስ ገዳም መንደር ያሉባቸውም የሌሉባቸውም አሉ ።

ስለዚህ አሁን መቀመጫውን በደምቢያ ያደረገው ግራኝ አህመድ እነዚህን ሁሉ ደሴቶችና ገዳማት አዳርሶ እንደበዘበዛቸው ዓረብ ፋቂህም ታሪከ ነገሥቱም አያወሱም ። ሁለቱም ያወሱት ስለደሴተ ገሊላ ብዝበዛ ብቻ ነው ። ይኸንንም ደሴት ለብዝበዛ የመረጠበት ምክንያት ምናልባት ከጐርጐራ አልፎ አሁን የሱስንዮስ ቤተ መንግሥት ፍራሽ ከሚገኝበት ቀበሌ በቆላ ድባ ወረዳ ውስጥ በተለይ ማንጌ ቀበሌ ሠፍሮ ሳለ ከሌሎቹ ደሴቶች ሁሉ ለዚህ ቀበሌ ቀርቦ የሚታየው የገሊላ ደሴት በመሆኑ ይሆናል ። ባይን ገመድ ሲለካ ከማንጌ ጠረፍ እስከ ገሊላ ደሴት ድረስ ምናልባት ፲ ቢበዛ ከ፲፭ ኪሎ ሜትር አይርቅም ። የቀሩት ግን ከዚህ የቀበሌ ጠረፍ ባይን እንኳ ለማየት ሩቅ ናቸው ። ወደ ገሊላ ደሴት እንኳን ገብቶ ለመዝረፍ ጀልባ በመሥራትና በጀልባ ሆኖ ሄዶ ደሴቱን የሚከላከሉትን ደምስሶ የመዝረፉ ነገር ለግራኝ በጣም አስቸግሮት እንደነበረ ዝርዝሩን ሁኔታ ዓረብ ፋቂሀ እንደዚህ ሲል ያመጣዋል ።

«በደምቢያ ጣፋጭ ውኃ ያለበት በታንኳ አራት ቀን የሚያስሄድ ሐይቅ አለ። በርሱም ውስጥ ፴ የሚሆኑ ደሴቶች አሉበት ። እነሱም የሸቱ (ዛፍና) ፍሬ በብዙ ያበቅላሉ ። ለእስላሞቹ መገዛት ያልፈለጉት የክርስቲያን ወታደሮቹም አለቆቹም ወደነዚህ ደሴቶች እየሄዱ ተቀመጡ ። ግብር እንዲገብሩ ከይማም መላክተኛ ቢሄድባቸው እምቢ ብለው መለሱና በየደሴታቸው መሽገው ተቀመጡ ። ኮባ በመሰለ ቅጠል ራሳቸው የሚሠሩት ታንኳ አላቸው ። ይኸም እነርሱ የሠሩት ታንኳ እንደ ወፍ እየበረረ በሩጫ ከእንጨት ከተሠራው ታንኳ ይቀድማል ። በመካከላቸውም ከአንዱ ደሴት ወደሌላው እየሄዱ የሚገናኙበትን መተላለፊያ ከሠሩ በኋላ በዚያ ያሉት መነኮሳትና ወታደሮች "እኛን ማንም ሊነካን አይችልም ። ያለነው በሐይቅና በደሴት ውስጥ ስለሆነ እንደኛ ታንኳውን መሥራት ከሚችል ሰው በቀር የሚነካን የለም" እየተባባሉ ክርስቲያኖቹና መነኮሳቱ ትምክህትና ኩራት አደረባቸው ። የመነኮሳቱን ዳንዴነት ዓለምንም የናቁ መሆናቸውን የሚያውቀው ንጉሣቸው ናብራዙን (ንቡረ ዕድ ?) የሚባለውን መነኩሴ በላያቸው መሪ አድርጎ ሾመላቸው ።

ይማምና እስላሞቹ በደምብያ ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ ታላላቅ ዛፎች እየቆረጡ ለታንኳ ሥራ ተከርክመው እንዲዘጋጁ አዘዘ . . . . . እያንዳንዱ ታንኳ ሰላሳ (ሰው) የሚይዝ እስኪሆን ድረስ ብዙ እንጨት ተዘጋጀ ። ለዚህም ለታንኳ

ሥራ አህመድ ቤን ሶለይማን ኢል ማህሪ የሚባለውን ሾመው ታንኳውንም የሚ
ሠሩ የዓረቦች ቍጥር ስምንት ነው ። ነገር ግን ይማም የሥራውን መዘግየት ተመል
ክቶ እንዲቀር አዘዘ ። ከዚያ ወደ ኑብያና ወደ ጐጃም ሄደና አገሩን አዘርፎ ብዙ
ምርኮ ማረከ ። በግድም ትቶት ከነበረው ከኤሚር ሻምኡን ጋር በጐጃም ላይ ተገ
ናኘ ።

ይማም ከሄደበት አገር ተመልሶ በደምብያ ሐይቅ (ጣና) ሲደርስ የታንኳው
ሥራ አልቆ ደረሰ (1) ። ወዲያው ወታደሮቹ ወደታንኳው ገብተው እንዲዋጉ አዘዘ
ወታደሮቹ ግን በእንደዚህ ያለው ሐይቅ አንተ ተጨምረህ ከአልገባህ ጦርነቱ ሊከ
ናወን አይችልም ወታደሩም ደህና አድርጎ የሚዋጋው አንተ ስትኖር ነው ብለው
መለሱለት . . . . . . ስለዚህ ይማም ባንደኛው ታንኳ ተሣፍሮ ሲገባ ዓረቦቹ በሌ
ላው ላይ እየተሣፈሩ ገቡ ። ከዚህ በፊት መለሳዮች በዚህ ዓይነት በታንኳ
ላይ ተሣፍረው የባሕር ጦርነትም አድርገው አያውቁም ። ታንኳዎቹም እየተን
ሣፈፉ ገሊላ ወደሚባለው ደሴት ደረሱ ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖቹ ከደሴታቸው
እርባ የሚሆኑ በታንኳ ተሣፍረው ወደ ሐይቁ መካከል እንደ ወፍ እየፈጠኑ መጥ
ተው ከእስላሞቹ ጋር ውጊያ ገጠሙ ። እስላሞቹም ወደነርሱ ተጠግተው በደንጊ
ያና በወንጭፍ ይዋጓቸው ዠመር ። የክርስቲያኖቹ ታንኳ ከሣር (ከኮባ) የተሠራ
ትናንሽ በመሆኑ እስላሞቹን ሊከላከል አልቻለም ። ስለዚህ እስላሞቹ ሁለት ሰው
የሚያስቀመውን ጥልቁን አልፈው . . . ወደ ደሴቱ መጡና ክርስቲያኖቹን
ተዋግተው አሸነፉዋቸው ምሥጋና ለእግዚአብሔር ይድረሰው . . . . . . ።

እርባ የሚሆኑ የደምቢያ ታላላቅ ሰዎች ከሹማምንቶቻቸው ከሸሪፍ ኤዲን
ቤን አሺ ፣ ከሸሪፍ መሐመድ ፣ ከሸሪፍ አብድራህማን ጋር ሆነው ወደ ይማም
መጡ እሱም በመልካም አቀባበል ተቀብሎ እስከ ኑብያ ድረስ የሚዘልቀውን አገር
ሰጣቸው ከደምቢያ ዠምሮ እስከ ኑብያ ያለውም አገር ሰላማዊ ሆነ ።

የእስላም ሃይማኖትን ከሁሉ ከፍ ያደረገው እግዚአብሔር ይመስገን . . . . .
ጌታ መሐመድም ምስጉን ይሁን . . . . . . ።

የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው የትሑቱ የሺሃብ ኤዲን ሼክ አህመድ ቤን
አብድርቃድር ቤን ሳሌም ቤን ኡስማን(ዓረብ ፋቂህ) በጁዘን (የመን) የሚቀመ
ጠው የመዠመሪያው መጽሐፍ ተፈጸመ ። አምላክ የርሱንና የዘመዶቹን የእስላም
ቹንም ሁሉ ኃጢአት ይቅር ይበል» (2) ።

እነሆ ዓረብ ፋቂህ የሚተርከው ታሪክ ወደ መጨረሻ አጻጻፉ እየደከመ የመ
ጣው እዚህ ፀጣና ባሕር እገሊላ ደሴት ብዝበዛ ላይ ሲደርስ ጨርሶ አቋርጦ ያቆ
ማል ።

ይኸን መጽሐፍ የጻፈው ከዚህ በፊት እንደአመለከትሁት ዓረብ ፋቂህ በግ
ማሹ ጦርነት ላይ ራሱ እየተገኘ ፣ ራሱ ሊገኝበት በአልቻለው ላይ የነበሩትን እነአ

(1) ይቅር ያለው ያረቦቹን ሥራ ሆኖ ሌላ ተሠርቷል ማለት ነው ።

(2) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 460 - 468

ISIC

ቡበክርን እንደዚሁም ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር የነበሩትንና በኋላ እየዞሩ ወደ ግራኝ የመጡትን እስላሞቹንም ክርስቲያኖቹንም ምርኮኞቹንም እየጠየቀ ከራሱ እንደበትም እየሰማ የጻፈው ነው ። መጽሐፉን ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት ሙሴ ረኔ ባሴት እንደገመቱት መጽሐፉን አዘጋጅቶ የፈጸመው እንደ አውሮፓ ቍጥር ፲፰፻፶፱ (እንደ ኢት. አቈጣጠር ፲፰፻፶፩ ዓ. ም.) ላይ ነው ።

በመጽሐፉ በመጨረሻ ላይ የትሑቱ የሺሃብ ኤዲን (ዓረብ ፋቂህ) የመዠመሪያው መጽሐፍ ተፈጸመ ስለሚል ፤ የጦርነቱን ታሪክ ያቆመው ባዔ ልብነ ድንግል ፴፪ኛው ዘመነ መንግሥት ንጉሡ ሊሞቱ ፫ ዓመት ግራኝም ሊገደል ገና ፩ ዓመት ሲቀረው እዚሁ ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ላይ ስለሆነ በዚህ ሁሉ ምክንያት ዓረብ ፋቂህ ሌላ የጻፈው መጽሐፍ እንዳለ አስመስሎታል ። ነገር ግን ይህ ሁለተኛው መጽሐፍ እስከዛሬ ጸሐፊ ፈልጎ ስለአላገኘው ያዔ ልብነ ድንግልና የግራኝ የመጨረሻው የጦርነት ዝርዝር ታሪክ ዓረብ ፋቂህ በሚሰጠው ዝርዝር ዓይነት አጥጋቢው ጽሑፍ ሳይገኝ መቅረቱ በጣም ያሳዝናል ። የብዙ ዠግና ታሪክም እንደተቀበረ መቅረቱ ነው ። የዠግኖቹ አርበኞቻችን የነአዝማች አዳሉ የነተሰፋ ልዑል (ዓቃጽን ሠራዊ) ታሪክ ዓረብ ፋቂህ ሳይጽፈው ቢቀር ኖሮ ተደብቆ ይቀር ነበር ። በዚህ ዓይነት የዓረብ ፋቂህ ጽሑፍ ካቋረጠበት ከ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ዠምሮ ግራኝ እስከሞተበት እስከ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ድረስ የተዋጉት የጀግኖች ታሪክ እንደተደፈነ ቀርቷል ፤ ታሪከ ነገሥቱም ስም ሲጠቅስ ዠብዱ መዘርዘር ስለማይሆንለት ስማቸውና ሞታቸው የተጠቀሰው በምን አኳኋን ተዋግተው እንደሞቱ አናውቅም ።

ስለዚህ ስለጠፋው ስለዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ጸሐፊ ሁሉ የሰጠው አስተያየት ልዩ ልዩ ነው ። ከተጻፈ በኋላ በጦርነት ተዘረፈ ወይም ተቃጠለ የሚሉ አሉ ። ማዦር ኔራሲኒ የሚባል የኢጣልያ መኰንን ከሐረርጌ የዚህኑ የዐረብ ፋቂህን መጽሐፍ አግኝቶ እንደሙሴ ረኔ ባሴት ሳያጣራ ወደ ኢጣልያንኛ ተርጉሞታል ።

እንደርሱም አሳብ ይህ ከገሊላ ብዝበዛ እስከ ግራኝ ሞት ድረስ ሊተርከ የሚገባው የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ሳይገኝ የቀረው ግራኝ ድል የሆነበት ይህ የመጨረሻው የታሪክ ጽሑፍ አያስፈልግም ብላ ሚስቱ ድል ወንበራ ስለአቃጠለችው ነው ብሎ ሰነድ ያልደገፈው የመላ ትችት ጽፏል ። ከርሱ በኋላ ይኸንኑ መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ፈረንሳዊኛ በተጣራ ዓይነት የተረጐሙት ሊቁ ሙሴ ረኔ ባሴት "ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ ወደ ፊት እጽፈዋለሁ እያለ ሲመኝ በመካከሉ ሞቶ ይሆናል" ብለው ሳያረጋግጡ እንደደንቡ አወላዋይ ወይም ሊመስል የሚችል አሳብ ለማቅረብ ተገድደዋል (1) ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው አጻጻፉ እየደከመ የመጣበትን ሁኔታ ስናመዛዝነው በእርጅና ይሁን ወይም በሕመም ወይም ጸሐፊና መሪ አንዳንድ ጊዜ የሚቀያየሙበት አይጠፋምና ጸሐፊው ከገሊላ ብዝበዛ በኋላ ከቤገምድር ወደ አገሩ ተመልሶ ሞቶ ይሁን አይታወቅም ቀደም ብሎ የተዳከመው ጽሑፍ እዚሁ ላይ ፈጽሞ

(1) ዓረብ ፋቂህ ፍቱሕ ኤል ሀበሽ የባሴት ረኔ ትርጉም መግቢያው ገጽ IV-VI

ተቋርጧል ። ስለዚህ አዘጋጅቶት ሳለ የግራኝ ሚስት አቃጠለችው ከሚለው መላ ይልቅ ሳይጨርሰው ሞተ የሚለው መላ የሚመስል ነው ።

እንግዲህ ወደፊት ለሚቀጥለው ለግራኝ አህመድና ላቤ ልብነ ድንግል እንደ ዚሁም ልብነ ድንግል ከሞቱ በኋላ ዓፄ ገላውዴዎስ ለፈጸሙት የጦርነት ታሪክ ዋና መሠረት የሚሆነው ባጫጭሩ የሚጽፈው የግዕዙ ታሪከ ነገሥትና የፖርቱ ጋል ተወላጆቹ እነሚጉኤል ደካስታንሖ፣ እነቤርሙዴዝ የጻፉት መጽሐፍ ነው ።

## ምዕራፍ ፺፮

## የግራኝ አህመድና የበላይ ሻንቅሎች ጦርነት - የግራኝ በሥልጣኑ መደላደል ።

ታሪከ ነገሥት ግራኝ በደምቢያ በተቀመጠበት ጊዜ የፈጸመውን አያመለክተንም ። ነገር ግን «በግንቦት ፳፫ ቀን መለሳይ (ግራኝ) ወደ ደዋሮ ሄዶ ፰ ወር ተቀምጦ በኋላ ተመልሶ በግንቦት ፳ ቀን አንጐት ደረሰ ። የንጉሡም የግዛት ዘመን ፴ ዓመት ሆነ» ይላል (1) ። ዓፄ ልብነ ድንግል በነገሡ በ፴ኛው ዓመት ይኸውም ማለት በግን ቦት ፳ ቀን ሲመለስ ዓመቱን ሙሉ ሲሄድ ወይም ሲመለስ ወይም ደዋሮ በነበረ በት ሰዓት የሠራውን አያወሳም ። ሲሄድ ወይም ሲመለስ እግረ መንገዱን እንደ ተለመደ አልገዛም ብሎ ከሚከላከል የክርስቲያን ጦር ጋር መዋጋቱንም ወይም በዚህ በደቡቡ ክፍል ያለው አውራጃ ሁሉ ከተወረረ ስምንት ዓመት ስለአለፈው ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛቱን አይነግረንም ። የዓረብ ፋቂህን መጽሐፍ አጉዳይነቱን በጎ ዘን የምንመለከተው ይኸን የመሳሰለው ታሪክ መኖሩ በአእምሮ እየታወቀ ካልተ ጻፈበት ባዶ ዘመንና ምዕራፍ ላይ ስንደርስ ነው ።

የዓፄ ሠርፀ ድንግልን (2) ዜና መዋዕል ያዘጋጀው ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ሃይ ማኖት የጌታውን የንጉሡ ንጉሥቱን የተዋጊነትና የመፈራት ዝና ለማመልከት ሲል ወደ ኋላው ተመልሶ ግራኝ አህመድ ደምቢያ የነበረ ጊዜ ከጐጃም ምዕራብ በበላያ በጣቁሳ በኩል የሚገኙት ሻንቅሎች በእርሱ አነጋገር "አግብርት - ባሮች" እያለ የሚጠራቸውን ኃይለኛነታቸውን ሰምቶ ሊዋጋ ሄዶ ሳይሆንለት ተሸንፎ አፍሮ መመለሱን በግዕዝ ጽፎታል ። እነዚህም ከጣቁሳና ከበላያ ወደ ምዕራብ የሚገኙት እስከ ሺሆጀሌ አገር ድረስ ያሉት ሻንቅሎችና ወርቅ የሚወጣባቸው አገ ሮች ጭምር ሳይሆኑ አይቀሩም ።

የሆነ ሆኖ የግራኝና የሻንቅሎቹ ጦርነት ከግዕዙ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደ ዚህ የሚል ነው ። «የእስላሞቹ ታላቅ የኢብራሂም ልጅ ኢማም አህመድ ሥልጣኑ ከአፍተል ባሕር (የዘይላ ወደብ) እስከ ድሆኖ ባሕር (የዛሬው አርኪቆ) ድረስ የተዘ ረጋው በደምቢያ የነበረ ጊዜ ከዚህ በፊት ነገሥታትም መኳንንትም ሲዋጋቸው የደ

(1) አመ ፳ወ፫ ለግንቦት ወሖረ መለሳይ ምድረ ደዋሮ ወነበረ ፰ አውራኀ ወተመይጠ እምህየ ወበ ጽሐ ምድረ አንጐት አመ፳ ለግንቦት በ፴ ዓመተ መንግሥቱ

(2) ሠርፀ ድንግል የነገሡበት ዘመን ፲፭፻፶፭ - ፲፭፻፹፱ ዓ. ም.

ፈረ የለም ማለትን ከአገሬው ሰው ስለሰማ እርሱ የአሸናፊዎች አሸናፊ የኃይለኞችን ዙፋን አፈራራሽ ስለሆን ሄዶ እነዚህኑ ባሮች (አግብርት) ይወጋቸው ዘንድ ከልቡ ቆርጦ ተነሣ ።

ስለዚህ ሠራዊቱን ፈረሰኛውንም እግረኛውንም ሰበሰበ ። ከዚያ በማሥጋሜ ሄዶ አገራቸው ደርሶ ሠፈረ ። ባሮቹም ከየአለበት እንደ አንበጣ በርክተው ተሰበሰቡ ። በእነዳደፍ የሠለጠኑ ስለሆኑ (ነዳፍያን) ፈረሱንም በቅሎውንም ሰዉንም እየመቱ ሰፈርም እንዳያደርግ ሰዉም እንስሳውም ውኃ እንዳይጠጣ አደረጉት ። በሰይፍ ቀርቦ ለመዋጋት የማይጠመዱ ሆኑ ። ነገር ግን በሩቁ ተደብቀው ይማቱ ዠመር ። በዚህ ምክንያት ይማም አህመድ ሌላ የመውጫ ደኅንነት ስላጣ በቶሎ ሸሽቶ ወደ ሠፈሩ በዕፍረት ተመለሰ» (1) ።

ወልደ ሃይማኖት ለማስገበር ከደምቢያ ወደ አገራቸው የመጣውን ግራኝ አህመድን ፊት ለፊት ተጋጥመው ሳይሆን በደፈጣ ጦርነት አሸንፈው አሳፍረው መመለሳቸውን ሲገልጽ በሩቅ ሆነው እየወረወሩ የተዋጉበትን መሣሪያ አይለይም ። በግዕዙ ሰዎቹን "ነዳፍያን ተናዳፊዎች" ተናደፉ ሲል ይነድፉ ነው የሚለው ። ይኸን ዜና መዋዕል ከግዕዝ ወደ ፈረንሳዊ የተረጐሙት ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ መሣሪያውን " FROND " ወንጭፍ ብለውታል ። ይኸ ቢሆን ኖሮ ግዕዙ ነዳፍያን በማለት ፈንታ ሰዎቹን ወጻፍያን ባለ ፤ ተናደፉ በማለት ፈንታ ወጸፉ ባለ ነበር ። ስለዚህ የሚመስለው በቀስት ነው እየመቱ (እየነደፉ) የመለሱት ።

ጸሐፊው የግራኝን በዚህ ዓይነት አፍሮ መመለስ ካመለከተ በኋላ ዓፄ ሠርፀ ድንግል ግን በሠራዊት ታጅበው ሊወጉዋቸው በሄዱ ጊዜ ሳይዋጉ እነዚሁ ሻንቅሎች ፍጹም ራቁታቸውን የሆኑ ሰውነታቸውን ግማሾቹ ቀይ ጭቃ የቀሩት ነጭ ጭቃ የተቀቡ መጥተው ገቡለት እያለ ታሪኩን ይቀጥላል ። የግራኝ ተሸንፎ አፍሮ መመለስና ዓፄ ሠርፀ ድንግል አሸናፊነት መካከል ምናልባት አንድ በትክክል ያልተጣራ ሁኔታ ይኖራል ። ግራኝ አህመድ በሌላው ጦርነት ላይ ሁሉ እንዳየነው አንድ ቦታ ሊዋጋ ሄዶ በጫካ ብዛት በተራራ ርዝማኔ በመንገድ እጦት ሳይመቸው የቀረ እንደሆነ እንደ አንድ ዳንዴ መሪ ወደፊት ግፋ በለው በማለት ሰውን እያስጨርስም ። ሁኔታውን በጥልቅ አጥንቶ ካመዛዘነ በኋላ አውቆ ውጊያውን ይተዋል ።

(1) እንዘ ሀሎ ኢማም አህመድ ወልደ ኢብራሂም በምድረ ደምቢያ ወውእቱ ዓቢዮሙ ለመለሳይ ዘመለከ ሥልጣኑ እምባሕረ አፍተል እስከ ባሕረ ደኾኖ ሶበ ሰምዓ ዜናሆሙ እምሰብአ ሀገር ወከመ ኢተሀበለ መኑሂ ፀቢአቶሙ እምቅድመዝ ኢእምነገሥት ወኢ እመኳንንት ። ውስተ ጊዜ አስተሐመመ በሕሊናሁ ወመከረ በልቡ ከመ ይፅብዖሙ እስመ ውእቱ መዋዒሆሙ ለመዋዕያን ወነሣቴ መናብርቲሆሙ ለኃያላን ። ወሶቤሃ አስተጋብአ ሠራዊቶ መስተፅዕናን አፍራስ ወሰብአ እግር በበጸታሆሙ ወእምዝ ተንሥአ ወሖረ እንዘ ይትጓዕ ወበጺሖ ኀበ ምድሮሙ ገብረ ከተማ ወእሉኒ አግብርት ተጋብኡ እምለፌ ወእምለፌ ወብዝኖሙ ከመ አንበጣ ወኮኑ ይነድፉ ቦቱ ሰብአ ወእንስሳ አፍራሰ ወአብቅልተ እስመ ነዳፍያን እሙንቱ በከመ ዘከርነ ቅድመ ወመካነሂ ከልእዎ ለሰፈር ወማየሂ ከመ ይስተዩ ሰብእ ወእንስሳ ከልእዎ ከመኒ ይጽብዖሙ በሰይፍ ኢይትራከብዎሙ ገጽ በገጽ አላ እምርኁቅ ቀዊሞሙ ወበኅቡእ ከዊኖሙ ይነድፉ ቦሙ ። በዝ ኩሉ ሶበ ኃጥአ ጥዒና ተመይጠ እንዘ ይትኃፈር ከመ ዘይጐይይ ወይደሀል ወበጽሐ ኀበ ከተማሁ ተኀፊሮ ። ታሪከ ነገሥት ዘሠርፀ ድንግል Historia Regis Sersa Dengel-Conti Rossini ምዕ. 9 ገጽ 114 - 115

ይኸም በጐጃም ምዕራብ ካሉት ግዕዙ አግብርት ከሚላቸው ሻንቅሎች ጋር ያደረገው የማሳመን ሙከራ ከዚሁ የዘደ መስመር አይዘልም ። ሰውን በከንቱ ላለማስጨረስ የወታደርን ሕይወት ለመቆጠብ አውቆ በተወበት ምክንያት ተሸንፎ አፍሮ ተመለሰ ለማለት ያዳግታል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ በአሁኑ ሰዓት ምንም እንኳን ንጉሡ ሁልጊዜ በሕይወት መኖራቸው በዙሪያቸውም ታማኝ ወታደርና ሹማምንት እንዳላቸው የታወቀ ቢሆን በየአውራጃው የተበታተነ ወይም በደፈጣ ጦርነት ሃይማኖቱን ወገኑን የሚከላከል ባይጠፋ በጠቅላላ የአገሪቱ ገዥነት ሥልጣኑም በዚህ ጊዜ ወልደ ሃይማኖት እንዳለው ከዘይላ ባሕር እስከ አርኪቆ ድረስ የተዘረጋና በሥልጣኑ የተደላደለ ገዥ መሆኑ የታወቀ ነው ።

በዚህም ሰዓት ንጉሡ ከዋስልና ከዓባይ ዳር ምርኮ እግዚአብሔር ከአተረፋቸው ወዲህ ሠራዊትም ቢኖራቸው ቅሉ ለመግጠም የሚያደባ የግራኝ ብትን ጦር እንዳይወጋቸው ለመከላከል እንጂ ግራኝን ራሱን ወይም ታላላቆቹን የጦር ሠራዊት የሚያዙትን አለቆች ፊት ለፊት እያባረሩ ለመግጠም አቅማቸውም ጊዜውም አይፈቅድላቸውም ። ነገር ግን በታማኝ ጦራቸው እየታጀቡ ግራኝ አህመድ ወይም አስፈሪው ድምር ጦሩ ያለበትን እያሰለሉ እርሳቸው ግን ከዚያ እየራቁ ታማኝና ተቀባይ ወደ ሆነው የክርስቲያን ወረዳ ከትግሬ ወደ ቤገምድር ከቤገምድር ወደ ጐጃም ከዚያ ወደ አማራ ወደ ግድም ከግድም እንደገና ወደ ትግሬ እየተዘዋወሩ ስለሚሠወሩ ግራኝም የርሳቸውን ዱካ እንደ ሐረግ እየተጠማዘዘ ማባረሩ ስለሰለቸው ደምቢያ ላይ ከትሞ በማረፍ ሌላ በጋብቻ የማግባቢያ ዘዴ ይፈልግ ገባ ።

ISJC

ስለዚህ ግራኝ አህመድ ንጉሡ ነገሥቱን መግደልም መማረክም ስለአቃተው የእርሳቸውም በዚህ ዓይነት በሕይወት መኖር ለአገዛዙ ሳንክ ስለሆነበት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በፖለቲካ ጋብቻ ተዛምዶ አገሪቱን ለመግዛት ጋብቻ መጠየቁን ታሪክ ነገሥቱ ያረጋግጣል ። ለጋብቻው ጥያቄ የእምቢታ መልስ በመጣለት ጊዜ በንዴት ያለውን ጦር ባዲስ ኃይል በመቀስቀስ ብዙ ጉዳት በንጉሡ ላይ ሲያደርስ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፺፮

## ግራኝ አህመድ ከዓፄ ልብነ ድንግል ልጅ ጋር ለመጋባት ጠይቆ ንጉሡ እንዳልተቀበሉት (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.)

ዓፄ ልብነ ድንግል ምንም እግዚአብሔር በዘመናቸው ይኸን የግራኝን ወረራ ቢያመጣባቸው በዘመናቸው ካሻሻሉት ነገር ውስጥ አንደኛው የጋብቻ ነገር ነው ። ከርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታት የግራ ባለቤት የቀኝ ባለቤት እያሉ ሁለት ሴት ያገቡ የነበረውን እርሳቸው በዘመናቸው እንደ መልካም የክርስቲያን ንጉሥ ባንድ ሴት በንግሥት ሰብለ ወንጌል ተወስነው በዚህም መጻሕፍት ሁሉ እንዳመሰገኗ

ቸው ከዚሁ ተያይዞ ዓጼ ልብነ ድንግል ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል ፡ ፊቅጦርን ፡ ገላው ዴዎስን ፤ ያዕቆብን ፤ ሚናስን ወንዶች ልጆችና ታየድራ ፤ ወለተ ቅዱሳን ፡ ሰበነ ጊዮርጊስ ፡ አመተ ጊዮርጊስ የሚባሉ ሴቶች ልጆች መውለዳቸው ፡ በዚህም ምክን ያት ብዙ ካገቡት አባቶቻቸው ባንዲት ሴት በሰብለ ወንጌል የተወሰኑት እርሳ ቸው ዘርና ተወላጅ በማበርከት ረገድ መብለጣቸውን ከዚህ በፊት አመልክተ ናል ።

እነዚህ ሁሉ በዚህ የጦርነትና የመከራ ዘመን ከአባታቸው ጋር ሳይለያዩ አብ ረው ይኑሩ ወይም ሴቶቹና ሕፃናት ከባለቤታቸው ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋር ግራኝ ሊወጣበት ወደማይችለው ወደስሜን ወይም ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ ወጥ ተው ይቀመጡ አይታወቅም ። ነገር ግን ወደፊት የፊቅጦርን ሲዋጋ መሞት የሚና ስን ከጦርነት ላይ መማረክ ስለምናነብ የቀሩት ቢቀር ለውጊያ የደረሱት ወንዶቹ ካባታቸው ጋር ሆነው ከግራኝ ጦር ጋር ከመከላከል ላይ ይገኙ ማለት ነው ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ግራኝ አህመድ ዓይነተኞቹን የኢትዮጵያ አው ራጃዎች ሁሉ ወርሮ በያለበት ሹማምንቱን ሹሞ እያስገበረ ገዥነቱ ከተመሠረተ ለት በኋላ የንጉሡ በሕይወት መኖር ለክርስቲያኑ ሕዝብ ተስፋ ለርሱ አገዛዝ ግን ሳንክ ስለሆነበት አባሮ ለመያዝ ፈትኖ ስለአልተሳካለት ባደረገው ጦርነት ለማ ደልም ለማስገደልም ስለአልቀናው በመጨረሻ እኚህን ንጉሥ በጋብቻ በአማችነት ሊማርካቸው ፈልጎ በነገሡ በ፴፩ኛ ዓመት ላይ "ልጅህን ዳርልኝና በመካከላችን ፍቅር ይሁን ይኸን እምቢ ያልክ እንደሆነ አምልጠኸኝ የምትሄድበት ቦታ የለም" ብሎ ዛቻ የተንተራሰ ልመና አቀረበላቸው (1) ።

ግራኝ አህመድ ይኸን የጋብቻ ጥያቄ ያቀረበላቸው ከደምቢያ ወደ ጐጃም ሄዶ እነመርጡለ ማርያምን አቃጥሎ በመስከረም ወር ደብረ ገሊላን ከበዘበዘ በኋላ በግንቦት ፳፫ ቀን ወደ ደዋሮ ሄዶ በስምንተኛው ወር ከተመለሰ በኋላ በአንጎት (በዋግና በአሸንጌ አካባቢ) ሳለ መሆኑን የታሪኩ ጽሑፍ ያወሳል (2) ።

ወደ ኢትዮጵያ ከገባ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ከቀድሞ ሚስቱ ከድል ወን በራ በቀር ምናልባትም ከሌሎች ከአዳልና ከሱማሌ ከዓረብ ዕቁባቶቹ ሌላ የተከለ ሃይማኖትን ሚስት ፡ የሐድያውን ገራድ ልጅ ፡ የመዘጋውን የሱልጣን መኩተርን ልጅ ሦስት ሴቶች ማግባቱን አንብበናል ። ሲያገባም በፖለቲካና በአስተዳደር በአገ ዛዝ ረገድ ያለውን የፖለቲካ ጥቅም በመመልከት እንጂ የሴቶቹ ውበትና ቁንጅና እየማረከው በዚህም ረገድ የሥጋ ፍትወቱን ለማስደሰት አለመሆኑ የታወቀ ነው ።

እስከ አሁንም ያገባቸው ባንዳንድ አውራጃ በሐድያ ወይም በመዘጋ ግዛት ዘሩን ለመትከል እንጂ በጠቅላላው በኢትዮጵያ ላይ ላለው የገዥነት ምኞቱ ከሐድ

(1) ወበ፴ወ፩ ዓመተ መንግሥቱ ለአከ ውእቱ መለሳይ ኀበ ንጉሥ እንዘ ይብል "ሀበኒአ ወለተከ ትኩ ነኒ ብእሲተ ወንግበር ፍቅረ ወለእመ ኢገበርከ ዘንተ ነገረ አልቦ ኀበ ዘታመስጠኒ" ታሪክ ነገሥት ገጽ 93

(2) መጽሐፈ ታሪክ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ ገጽ 119

ያና ከመዘጋ ባላባቶች መጋባቱ ምንም ያህል ሊጠቅመው አይችልም ። የተክለ ሃይ ማኖትንም ሚስት ማግባቱ ምንም እንኳ ሴትዮዋ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ዝምድና ቢኖራት በዘሩ ርቀት ምክንያት በዚህም ላይ ከምርኮ ላይ ተይዛ በግድ የተገባች በመሆኗ ከገባች በኋላ በማደሪያ ጭምር ምንም ከግራኝ ጋር ተዋሕዳ ብትቀመጥ በዚች ሴት ጋብቻ ምክንያት ተስቦ የገባለት ነገድና ወረዳ መኖሩን አላነበብንም ። የቅርብ ዘመዷ አይበስ ለሐዔ እንኳን ከገባለት በኋላ ሃይማኖቱን ክዶ መስለሙ ጸጸት ሆኖበት ለግራኝ በገባ በሦስተኛው ወር አምልጦ ወደ ንጉሡ እንደተመለሰ ያነበብነው ትዝ ይለናል ። የልብን ጥልቃዊ እምነትና ምኞት ኃይልና ጋብቻ ብቻቸ ውን ሊደመስሱ አይችሉም ። ይኸን በመሳሰለ ድለላ አቅዋማቸውን የሚለዋውጡ በፍጥረታቸው እንደነ አናንያ አድር ባዮች የሆኑት ብቻ ናቸው ።

የሆነ ሆኖ በርሱ አስተያየት ከሁሉ ይበልጥ የንጉሡ ነገሥቱን ሴት ልጅ ማግ ባት ከጦር ሠራዊቱና ከኃይሉ ጋር ተደራቢ መሠረት እንደሚሆን ስለሚያስብ እላይ ያነበብነውን ዛቻ ያለበት የጋብቻ ልመና ወደ ንጉሡ ለመላክ ተገደደ ። የል መናውም አኳኋን ምንም እንኳን ንጉሡን በመዳፉ ውስጥ ጨብጦ ያልያዛቸው ቢሆን "ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ" ከሚባለው ጋር ይመሳሰላል ።

በዚህ የጋብቻ ገመድ ንጉሡን ስቦ በሥልጣኑ ውስጥ ለማስገባትና ምዕመናኑ ሕዝብ በየጫካው በየተራራው የሚከራከረውም ንጉሣችን ከግራኝ ተጋብተው ከታ ረቁ እኛም እንግባ እንታመን እየገበርን [illegible]ኑር ብሎ በመንፈሱ እንዲረታለትና የበላይ የገዥነት ሥልጣኑን እንዲያውቅለት ነው ።

ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል ምንም ቢሸነፉ ኃይላቸውም ቢመ ነምን ቅሉ እንደ ሐድያውና እንደ መዘጋው ባላባቶች አይደሉም ። ከላይ ከዳዊት ከሰሎሞን ዘር በመውረዳቸው የሚመኩ የቅርቦቹ የነዘርዓ ያዕቆብ ፡ የነበእደ ማር ያም የልጅ ልጅ የናዖድ ልጅ በመሆናቸው የሚኮሩ የመላዋ ኢትዮጵያ ጌታ ለመሆን ከእግዚአብሔር መቀባታቸውን የሚያምኑ ስለሆኑ የዚህ ሁሉ ስሜት በዚህ በመከራውና በጭንቁ ሰዓት ከአሳባቸው ሊጠፉ አልቻለም ። ይኸን ስሜት እላይ እንዳልነው የመድፍ ጥይት ያዳዲስ ነፍጥና የጠላት ወታደር ብዛት ዘወትር የመሸነፉ ዘወትር የመሰደዱ መከራ ሊሠርዘው አልቻለም ።

ግራኝ አህመድ በሩቁ በታላቁ በቱርክ መንግሥት በቅርቡ በግብፅና በዘቢድ በአደን ታሻዎች መደገፉን ባጠገቡ ከባሕር ማዶ የመጡት የቱርክና የፋርስ የሕን ድና የዓረብ ወታደሮች የኃይሉ መሠረት መሆናቸውን እነሱም በወታደራቸው የማይበገሩ መሆናቸውን ቢያውቁም ፤ የራሱን የግራኝን ፅኑካኝነቱን ተንኮሉን ዘዴ ውን ግብዝናውን በጠቅላላው አሁን ያለበትን ያሸናፊነት ደረጃ ከማንም ይበልጥ ቢገነዘቡትም ፤ በዚያው አንጻር የርሳቸውን መዳከም የጦር ሠራዊታቸውን መመ ንመን የአብዛኛውን ሕዝብ ለግራኝ መግባት በትክክል ቢረዱትም ፤ ለርሳቸው ሊረዱ ተስፋ የሰጡት በወጠኑት ዝምድና ይኸን የጦርነት እሳት በበለጠ እንዲንቀ ለቀል ያደረጉት ፖርቱጋሎች ድምፃቸው ቢጠፋም ከጸናው እምነታቸው ሊነቃነቁ አልቻሉም ። እዚህ ላይ የመንፈሳቸው ታላቅነት በግልጽ ይታያል ።

በዚህ ሁሉ ችግርና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ንጉሠ ነገሥት

ሴት ልጃቸውን ለዚህ ለጨካኝ ጠላታቸው ድረው ኢትዮጵያ የግላቸው አገራቸው መሆኗ ቀርቶ የጋራ አገዛዝ ወይም ሰላም ከማግኘት ይልቅ የንጉሥ ነገሥትነት ክብራቸውን እንደተጐናጸፉ መከራውን ለመቀበል ወይም ለመሞት ስለወሰኑ ከግራኝ ዘንድ ከዛቻ ጋር ለተወረወረው የጋብቻ አሳብ ሳያወላውሉ እንደዚህ ሲሉ ቁርጠኛ መልስ ሰጡ ። «አንተ አረመኔ ሆነህ እንደምን አድርጌ ልጄን እሰጥሃለሁ ። ይኸን አድርጌ ባንተ እጅ ከመውደቅ እንደ ኃይሉ ምሕረቱ በበዛው ለደካሞች ኃይልን ለኃይለኞች ድካምን በሚሰጠው በእግዚአብሔር እጅ መውደቅን እመርጣለሁ» (1) ።

መቼም ግራኝ አህመድን "አንተ አረመኔ ስትሆን ልጄን ላንተ እንዴት እድራለሁ" ሲሉ የግራኝ አረመኔነት ሕዝብ መፍጀቱና የጭካኔው አድራጎት ነው እንጂ በእግዚአብሔር የሚያመልክ ከአረመኔነት ውጭ ነው ። በዚያን ጊዜም በዛሬውም አጻጻፍ አረመኔ ተብሎ የሚጠራ ባንድ አምላክ ሳያምን አምላክ በፈጠረው ሥነ ፍጥረት በፀሐይ በጨረቃ በእንስሳ የሚያመልክ ነው ።

ይሁን እንጂ ቀድሞ ባንድ እግዚአብሔር የማያመልኩት በብዙ አማልክትና ጣዖት የሚያምኑት የግሪክና የሮማውያን ተወላጆች ከነርሱ ውጭ የሆነውን ሕዝብ ሁሉ "ባርባር - አረመኔ" ይሉት እንደነበረው ከቀድሞው ዠምሮ አይሁድ ክርስቲያን እስላም ሁሉ የየግሉን እምነት በማጽደቅና በማሞገስ የቀረውን እንደ አረመኔ መቁጠሩ የተለመደ ስለሆነ አሁንም ዓፄ ልብነ ድንግል ግራኝን እንደ አረመኔ የቆጠሩት በሃይማኖቱ ሳይሆን በተግባሩ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ የዓፄ ልብነ ድንግል ቁርጠኛ መልስ ለግራኝ ከደረሰው በኋላ የአለውን ኃይል እንደገና ቀስቅሶ በንጉሡና በቤተ ሰባቸው ላይ ከፊተኛው የበለጠ የጦርነት አደጋ ማውረዱን ወደፊት እንመለከታለን ። ይኸውም ሆኖ በጦርነት እንደ ተለመደ ቢያሸንፋቸውም ቢያሳድዳቸውም አንዱን ልጃቸውን ለመግደል ሌላውንም ለመማረክ ቢችልም እርሳቸውን ግን ሊያሸንፋቸው እንጂ በምርኮ ይዞ ወይም በጋብቻ ወጥመድ ጠልፎ ፈጽሞ ሊያዋርዳቸው ሃይማኖታቸውንም ሊያስለውጣቸው አልቻለም ። እንኳን እርሳቸው ሊለውጡ በበታቻቸው ያለውም ሕዝባቸው ምንም የመከራና የሞት ሥቃይ ቢበዛበት ሃይማኖቱን እንዳይለውጥ ከዚህ ቀጥሎ ባለው የሥላሴ ቅኔ አስጠንቅቀዋል ።

ኢትክሀዱ ስሞ ለኢየሱስ ዘሐመ ወሞተ በእንቲአከሙ ።
እንዘ ይክዕዋ ለንጽሕት ደሙ ።
ከመ ትኩኑ ውሉዶ ወመዋርስቲሁ አንትሙ ።
እመኒ አረሚ ጼወወክሙ ወለእመኒ መጥባሕት አሕመመክሙ ።
ፍዳ ግፍዕ ይጸንሕ ለክሙ ። (2) ።

(1) ንጉሥኒ ሜጠ ሎቱ እንዘ ይብል "እፎ እኁበከ እንዘ አረማዊ አንተ ፣ ወይኄይሰኒ ወዲቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር እምእደቅ ውስተ እዴከ ። እስመ በከመ ዕበዩ ከማሁ ብዝኀ ምሕረቱ ። ይሁብ ኃይለ ለድኩማን ወድካመ ለጽኑአን ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 93 ። ጥቅሱ የተወሰደው ከዳዊት መዝሙር 75 ፤ 8 - 11 ። 145 ፤ 14 ነው ።

(2) መጽሐፈ ቅኔ - መልአከ ብርሃን አድማሱ የሰበሰቡት ገጽ 236 ።

## ምዕራፍ ፺፰

## የጦርነትና የመከራ ጽናት - የአቤቶ ፊቅጦር ሞት ሚያዝያ ፲፬ - የአቤቶ ሚናስ መማረክ ግንቦት ፳፭ ቀን ፲፭፻፴፩ ዓ. ም.

ግራኝ በዛቻ ልጅዎን ያጋቡኝ ብሎ ከጠየቃቸውና እርሳቸው ደግሞ ስድብ ጨም ረው ላንተ ለአረመኔ እንደምን እሰጣለሁ ብለው ከመለሱለት በኋላ ከግራኝ በኩል የጦርነቱን በኃይል መቀስቀስ እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ ሰላም እንደማይጠብቁ የታ ወቀ ነው ።

ስለዚህ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የሆነውን የጦርነቱንና የመከራውን ሁኔታ ባጭሩ ግዕዝኛው ታሪክ እንደዚህ ሲል ከጋብቻው እምቢታ አከታትሎ ያመጣዋል ። «በዚያን ጊዜ በንጉሡና በሠራዊቱ ታላቅ መከራና ብዙ ስደት ረሃብና ጦርነት ደረሰ ፤ ቀጭኑ አቡበከር በመንገድ በድንገት ሚያዝያ ፮ ቀን በዕለተ ረቡዕ በሕማ ማት ሰሞን ተዋጋቸው ። አዛዥ ተክለ ጊዮርጊስና አዛዥ እምኃ ፣ ሚካኤልና ዳረ ጎት ፤ ያዕቆብና ጋድ የቢዘኑ ተወላጅ የደብረ ሰማዕቱ መምህር አባ ተንሥአ ክርስ ቶስ ዓመተ ልዑልና ሌሎቹም ሞቱ ። ጉዴዎንና የንጉሡ አማት ዮዲት ከብዙ ሠራ ዊት ጋር ተማረኩ ቍጥር የሌለው ገንዘብ ጠፋ» (1) ፤ ብሎ የጦርነቱን አኳኋን ዓረብ ፋቂህ አስለምዶን እንደነበረው ሳይዘረዝር ባጭሩ በሚያዝያ ስድስት ቀን ባልጠረጠሩበት ሰዓት ድንገት ቀጭኑ አቡበከር በመንገድ ደርሶ ወይም አድፍጦ ጠብቆ በመዋጋት ይኸን ያህል የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሰው ፈጅቶባቸ ዋል ማለት ነው ።

ISIC

በሹም ሽሩ ላይ እንዳነበብነው ከቤገምድር ዠምሮ መላውን የአማራና የላ ስታ አገር የተሾመው አቡበከር ነው ። ክርሱም ጋር ያገር ተወላጆቹ የበለው ነገ ዶች ከሹማምንቶቻቸው ከሹም መሐመድና ከሹም ሹክር ጋር መደልደላቸውን ያነበብነው ትዝ ይለናል ። ስለዚህ በነዚህ በውስጥ አወቆቹ በበለው ነገዶች ጥቆ ማና ትጋት ቀጭኑ አቡበከር ወዲህ ዋና ተዋጊ ወዲህም አገረ ገዥነቱ የራሱ በመ ሆኑ ምናልባትም በሕማማት ጾም ሰውነታቸው በደከመበት ሰዓት አድብቶ በዋ ናው ሠራዊት ላይ ከፍ ያለ የግዳይና የምርኮ አደጋ ጥሎ ንጉሡ ለጥቂት አምልጠ ዋል ማለት ነው ።

ይኸን መጽሐፍ ከሥር ዠምሮ እያነበበ እስከዚህ ምዕራፍ የደረሰ አንባቢ አቡበከር ቀጭኑ ማን መሆኑን እንደማይዘነጋው እምናለሁ ። ገና ከ፲፪ ዓመት በፊት ራስ ደገልሃን አዳል ዘምቶ እናቱን ጭምር ማርኮ የተመለሰ ጊዜ ከግራኝ ጋር

(1) ወእሜሃ ኮነ መከራ ዓቢይ ወስደት ብዙኀ ሳዕለ ንጉሥ ወሠራዊቱ ረሀብ ወተይናት ወጸብዖሙ ቀጭን እቦከር በፍኖት እንተ ኢተሐዘቡ አመ ፮ ለሚያዝያ ወዕለቱ ረቡዕ ሰሙነ ሕማማት ወሞቱ አዛዥ እምሐ ወሚካኤል ወዳረጎት ወያዕቆብ ወጋድ ወአባ ተንሥአ ክርስቶስ ዘቢዘን መምህር ዘደብረ ሰማዕት ወዓመተ ልዑል ወካልአን ብዙኃን ። ወተጼወዉ ጉዴዎን ወዮዲት ሐማተ ንጉሥ ወብዙኃን ሠራዊተ ንጉሥ ምስሌሆሙ ። ንዋይኒ ጠፍአ ዘዓልቦ ኍልቍ ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 93 ። ሬኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 329 ።

እስከ ደዋሮ ተከታትሎ መጥቶ ከደገልሃን ጋር ተዋግቶ እናቱን በውጊያ ያስጣለና በዚሁ «አሸናፊ ልጅ ለሕዝቡ ሊከላከል ተነሣ ፣ ተጋዳይ ልጅ የሕዝቡን በደል ከፈለ» ተብሎ የተገጠመለት ነው ።

በምዕራፍ ፴፫ ላይ እንዳነበብነው ወደ ክርስቲያኖቹ ዞሮ እየወጋ ያናደደውን የቃግማውን ተክለ ሃይማኖትን ግራኝ "ከነሕይወቱ ማርከህ ካላመጣህልኝ ጉበዝ አልልህም" ብሎት ሄዶ ማርኮ ያመጣበትን ታሪክ አንብበናል ። በተረፈ ቀጭኑ አቡበከር በየቦታው የሠራው በየምዕራፉ ተጽፏል ።

እላይ እንዳነበብነው ግራኝ አህመድ ከሦስት ዓመት በፊት ሰሜንና ወገራን አስገብሮ በደምቢያ የነበረ ጊዜ ሹመት ሲደለድል ከቤገምድር ዠምሮ የላስታንና የሰቆጣን የዋግን ግዛት እንደሰጠው አንብበናል ። ስለዚህ ግራኝ አህመድ የዓጼ ልብነ ድንግልን የጋብቻ እምቢታ ከሰማ ወዲህ በል እንግዲህ አንዠቱን አርሰኝ ብሎ አዞት ይሆናል ። ነገር ግን ንጉሡ ስላመለጡ የግራኝ አንዠት በሙሉ ሊርስ አልቻለም ።

ከዚህ በላይ በጦርነት ከሞቱት ውስጥ አዛዥ ተክለ ጊዮርጊስ ግርማ ዣን ከሚባለው ጋር ግራና ቀኝ አዛዦች ከነበሩት አንዱ ሳይሆን አይቀርም ። እምሐም ከአዛዥ ዮናዳብ ጋር የዣን ደረቦች ሹም የነበረ ነው (1) ። እርሱም ከዚህ በፊት ከሰይፉ ጋር ሆኖ በደዋሮና በሌላም አውራጃ ብዙ ጊዜ ተዋግቷል ። በተምቤንም ከፋኑኤል ጋር ሆኖ መዋጋቱን ከሦስት ዓመት በፊትም ፋራ ቃሃም የሚባለውን የግራኝን የጦር አለቃ መግደሉን አንብበናል ። ዳረጐት ያለው ደሀርጐት (ደሀር ጐይታ) የሚባለውን ነው ። እርሱም በባሌ በጋፋት በዳሞት በቤተ አምሐራ ሲዋጋ የኖረ ነው ። ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ ንጉሡ ነገሥቱ ወደ ዋስል መጥተው የተቀመጡ ጊዜ ወደ ዋስል የሚያስገባውን ፪ በር በታላላቅ የጦር አለቆቻቸው በእዛዥ ደገልሃንና በራስ ነቢያት ያስጠበቁ ጊዜ ሦስተኛውን በር ያስጠበቁት በደሀርጐት ነበር ። እንግዲህ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እነዚህ ሁሉ ካለፈው የጦርነት ወቅት ከምርኮና ከሞት ተርፈው ለጌታቸውና ላገራቸው በታማኝነት ሲያገለግሉ ኖረው አሁን ከአቡበከር ቀጭኑ ጋር ሲዋጉ ሞተዋል ማለት ነው ። ዝርዝሩን ብናጣው ነው እንጂ እነዚህ ሁሉ ታላላቅ የጦር አለቆች የሞቱት ታላላቅ ጦርነት ተደርጎ ብዙ የጀግንነት ሥራም እንደተፈጸመ የታወቀ ነው ። ከነዚህም ጋር ዓመተ ልዑል የተባለችው ከንጉሣዊ ቤተ ሰብ አንዲቷ ከቢዘኑ ተወላጁ ከደብረ ሰማዕቱ መምህር ከአባ ተንሥአ ክርስቶስ ጋር መሞቷን ሲያመለክተን የሞተችበትን ምክንያት አይገልጽም ። ምናልባት እስከአሁን ድረስ ዓረብ ፋቂህም ታሪከ ነገሥቱም የሴት ተዋጊ ጠቅሰው አያውቁምና የራሷና የወገኖቿ ጥቃት ተሰምቷት ሴትዮዋ እንደ ወንድ ስትዋጋ ሞታ ይሆናል ። እንደዚሁም የንጉሡ ያዒ ልብነ ድንግልን የሚስታቸውን እናት ዮዲት የሚባሉትን ከጌዴዎንና ከብዙ ሀብት ጋር መማረካቸውን ሲገልጽልን ጌዴዎን የዮዲት ባል የእቴጌዪቱ አባት ወይም የእንጀራ አባት መሆን አለመሆኑን አያወሳም ። አብዛኛ ጊዜ ጌዴዎንና ዮዲት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የሚጠ

(1) Liber Axum-Conti-Rossini ገጽ 41

ሩበት ፈላሾቹ ናቸው ። እቴጌዪቱ ከሰሜን ባላባት እንደሚወለዱ አንብበናል ። ስለዚህ ጌዴዎንና ዮዲት ከላይ የፈላሻ ተወላጅነት ኖሮአቸው በኋላ ክርስትና ተንሥተው ከንጉሡ ተጋብተው እንደሆነ አይታወቅም ።

ይኸም ሁሉ ሆኖ ግራኝ በዚህ በተደረገው ጦርነት ባገኘው ድልና ምርኮ በእስ ገደለው ሹማምንት ብዛት ተደስቶ በንጉሡ ነገሥቱ ላይ የሰነዘረውን አዲስ የቁጣ ጦርነት አላቆመም ። እነአዛዥ ተክለ ጊዮርጊስ እና ደሀርጎት በሞቱ በስድስተኛው ቀን በሚያዝያ ፲፪ ቀን ገራድ ኡስማን ከበኩር ልጃቸው ከፊቅጦር ጋር ተዋግቶ በጦርነቱ ፊቅጦር ከዮናዳብ ከክፍሎ ከዮሴፍ ከዓምዱ ከሳል ወናግ ጋር ሞተ የሚሉ ከፍ ያለ የኀዘን መርዶ ደረሳቸው (1) ።

ከዚሁ አከታትሎ አሚር ኡመር የሚባለው ፊቅጦር ከነጓደኞቹ በሞተ በሁለተኛው ወር በግንቦት ፳፭ ቀን ራሳቸውን ገጥሞ ወጣቱ ልጃቸው ሚናስ ተማረከ ። በዚህ ጦርነት ዕዝራ የሚባለው የውስጥ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ፣ ግራ ጌታ ጊዮርጊስ ፣ ባሕርይ የማርታ ልጅ ከብዙ ሌሎች የክርስቲያን አለቆች ጋር ሞቱ ። ግማሾቹም እየተማረኩ ተሸጡ ። ግዕዝኛው ታሪክ ነገሥት ይኸን ቃል ከጻፈ በኋላ መደምደሚያውን «በሠራዊቱ መማረክና በልጁ መያዝ ንጉሡን አጥብቆ ኀዘን ተጫነው ይኸም ሁሉ የሆነው በዋግ ውስጥ ዛታ በሚባለው ሥፍራ ነው» ይላል (2) ።

ስለዚህ ኃያላን የጦር አለቆቹን ገራድ ኡስማንን አቡበከር ቀጢንን ፣ ኤሚር ኡመርን በየበኩላቸው ልኮ ውጊያውን በ[illegible]ና በጥድፊያ ይዞ ንጉሡን አሳዶ ለመያዝ የዛቸውን ቃል በሥራ ለመፈጸም እንዳሰበ ይታወቃል ። ይሁን እንጂ ምንም የበኩር ልጃቸው ፊቅጦር ቢሞት የቀሩትም ከብዙ ሀብትና ከወለዱት ልጃቸው ከሚናስ ጋር ቢማረኩ ዋናው የተፈለገው የርሳቸው የንጉሠ ነገሥቱ እጅ አልተገኘም ።

በንጉሡና በወገኖቻቸው ላይ አደጋ የጣለው የመዠመሪያው ጦርነት የተደረገው ሚያዝያ ፯ ቀን ረቡዕ በሰሙነ ሕማማት መሆኑን ታሪክ ነገሥቱ ገልጿል ። የግራኝ ጦር በሌላውም ቀን ቢሆን በዚህ ዘመን አለመቻሉ ግልጽ ቢሆንም በተለይ ረቡዕን የሕማማትን ቀን የመረጠበት ምክንያት ምናልባት በዚህ በሕማማት ሳምንት ክርስቲያኖች እስከማታ ድረስ እየጾሙ እህል አይቀምሱም በዚህ ጊዜ ብንገጥማቸው በረሃብ ደክመው እጃቸውም ለውጊያ ይዝላልና በቀላሉ ይሸነፋሉ የሚሉ የምክር አሳብ ይኖርበት ይሆናል ።

እውነትም በሌሎች ባለፈ ጦርነቶች ጊዜ ያልተገኙ ውጤቶች በዚህና ተከታትሎ በፋሲካ ማግስት (ሚያዝያ ፲፪) በተደረገው ጦርነት ለግራኝ ተገኝተውለታል። ላዩ ልብነ ድንግልም የፊቅጦር ሞትና የሚናስ መማረክ ከመቸውም የበለጠ ታላቅ የአደጋ በትር መሆኑ አይጠረጠርም ። በዚህ ምክንያት ነው ታሪክ ነገሥቱም ባጭሩ "ወተዳደቆ ኀዘን - ኀዘን ተጫነው" ሲል ያነበብነው ።

(1) ወበውእቱ ጊዜ በጽሐ ለንጉሥ ዓቢይ ኀዘን ወሞተ ወልዱ ዘበኵሩ ፊቅጦር . . . . . . .
(2) ወተዳደቆ ኀዘን ለንጉሥ በተፄውወተ ሠራዊቱ ወተእኅዞተ ወልዱ ። ዝ ኮነ በምድረ ዋግ ዘትሠመይ ዛታ ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 93 ። ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 329 - 330 ።

የፊቅጦር ገዳይ ገራድ ኡስማን ባለፉት ምዕራፎች እንደምናስታውሰው ንጉሥ ነገሥቱ በተሸነፉባቸው በሽምብራ ኩሬና በዋስል በወገራ በስሜን ብዙ ጦር ነቶች የተካፈለ ከወዚር አባስ ጋር ሆኖ በሠራዬ ተሰፋ ልዑልን የወጋ እርሱ ነው ። ይኸን ሰው ወደፊት ዓፄ ገላውዴዎስ ተዋግተው ሲያሸንፉት እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፺፱

### የኢሚር ኡመርና ያፄ ልብነ ድንግል ፬ኛው ጦርነት (፲፭፻፴፩ ሰኔ ፲፯)
### የኡመር ባንድ ተራ ሰው እጅ ተወግቶ መሞት (፲፭፻፴፪ ዓ. ም.)

ኤሚር ኡመር ግንቦት ፳፰ ቀን ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ተዋግቶ ማሸነፉ ሚናስን መማረኩ እነዕዝራን እነግራ ጌታ ጊዮርጊስን መግደሉ አልበቃውም ። ዋናው የግራኝ አህመድ ዓላማ ንጉሠ ነገሥቱን መማረክ ወይም መግደል ስለሆነ ንጉሡ ከዋግ ወደ ሰለዋ በሸሹ ጊዜ ተከታትሎ ሄዶ በሰኔ ፲፯ ቀን እንደወጋቸው ታሪክ ነገሥቱ ያረጋግጣል ። ከዚሁ አያይዞ በሰላዋ ኡመር ደርሶ የወጋቸው ጊዜ ከጥቂት ወታደር ጋር አምልጠው ወደ ጸለምት ሄደው ባንድ ጭልምፍራ (ጽልምፍራ) በሚባል ተራራ መቀመጣቸውን ፤ ከዚያም ያገሩ ጌታ ኢዮራም ካንድ እስላም ጋር ተባብሮ በሐምሌ ፲፬ ቀን እንዳሳደዳቸው ፤ ከዚያ በእግዚአብሔር እርዳታ የተከዜን ወንዝ በእግር ተሸ[illegible]ረው ታቦር በሚባለው በሺሬ ውስጥ ከፍተኛ በሆነ ተራራ እንደከረሙ አከታትሎ ያመጣና በንግሡ በ፴፪ኛው ዓመት እግዚአብሔር ድልን ስጥቷቸው በመስከረም ፳፯ ቀን (፲፭፻፴፪ ዓ.ም.) አህመድ ዲንን መግደላቸውን ከዚሁ አያይዞ በጥቅምት ፩ ቀን ከዋናው አሳዳጅ ባላጋራቸው ከኡመር ጋር ተጋጥመው ይኸው ኡመር በጦር ተወግቶ መቁሰሉን ከአመለከተ በኋላ ከዚሁ አያይዞ ኡመር እንደቆሰለ ሳይሞት ከደምቢያ ወደሺሬ ሄዶ ከዚህ በፊት ሳይቃጠሉ ተርፈው የነበሩትን የመጥበቢላን ቤተ ክርስቲያን በታኅሣሥ ፲ ቀን ፤ የጉትማንን በታኅሣሥ ፲፭ እቃጥሎ እንደ አጠፋቸውና ብዙ መነኰሳት እንዳለቁ ከዚያም የከብርቶን የደብረ ከርቤን አብያተ ክርስቲያን ዘርፎ ወደ ሺሬ ተመልሶ ከዚያ ወደ በለይጤና ሄዶ እንደቆየ እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳየው ዘንድ ከሚስቱ ጋር አልጋ ላይ በተኛበት ሰዓት አንድ ስሙ ያልታወቀ ደሀ ገብቶ ሆዱን ስንዝር እስኪሞላ ድረስ በሾተል ቀዶ እንደገደለው ያረጋግጣል (1) ።

በዚህ አተራረክ ላይ ኡመር ዓፄ ልብነ ድንግልን ከዋግ (ላስታ) ወደሰለዋ ከሰለዋ ወደ ጸለምት ወደሺሬ በማሳደድ እየወጋ አሸንፎ በመጨረሻ ከጥቂት ሰዎች ጋር ሺሬ በሚገኘው ከፍ ያለ ተራራ ከተቀመጡ በኋላ በመስከረም ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፪ አህመድ ዲንን ለመግደል የቻሉት በምን አኳኋን ከሸሹ እንስራርተው ምን አዲስ ኃይል አግኝተው እንደሆነ ታሪክ ነገሥቱ ሳይገልጸው መቅረቱ የታሪኩን ጉድለትነት ያሳያል ። ከዚሁ አከታትለው ባለፈው ዓመት በግንቦት ፳፰ በሰኔ ፲፯ በሐምሌ ፲፬ ቀን ከአውራጃ ወደ አውራጃ ያሳደዳቸውን ኡመርን በዚህ ዓመት

(1) ፈነወ አሐደ ነዳየ . . . ውእቱሰ ነዳይ ቦአ ኃቤሁ . . . ወረገዞ መልእልተ ኅንብርቱ ወሰጠጠ መጠነ ስዝር . . . . ታሪክ ነገ. ገጽ 331 ።

በ፲፰፻፴፱ ዓ. ም. በሁለተኛው ወር በጥቅምት ፳ ቀን ጦርነት ገጥመው ሊያቆስሉ የቻሉበት ኃይል ለጊዜው በግልጽ አይታይም ።

መቼም በ፲፰፻፳፬ ዓ. ም. ዋስል ላይ በ፲፰፻፳፯ ዓ. ም. ዓባይ ላይ ሊማርካቸው ተጣጥሮ ሳይሳካ ከቀረ ወዲህ ግራኝ አህመድ በጥብቅ እርሳቸውን የመከታተሉን ጉዳይ ችላ ብሎ ሌሎቹን ያልተያዙትንና ለሥልጣኑ አሜን ብለው ያልገበሩትን አገሮች የአማራን አገር አንጎትን ፡ ላስታን ፣ ትግሬን ጸለምትን ወገራን ስሜንን ቤገምድርን ጐጃምን በማስገበር ከ፲፰፻፳፯ ዓ. ም. እስከ ፲፰፻፴ ዓ. ም. ያሉትን ዓመቶች አሳልፏል ። ንጉሡ ንጉሠ ነገሥቱም የርሱን አቅጣጫ ያለበትን አውራጃ እያሰ ለሉ ራቅ ባለው አውራጃ ወዲያና ወዲህ እያሉ ከታማኝ ሠራዊታቸውና ከቤተ ሰባ ቸው ጋር የውጊያ ጽናት እምብዛም ሳይጫናቸው ቆይቷል ። በዚህም ላይ ምንም በያለበት ቢሰደዱ አሁንም የርሳቸውንም የራሱንም ሕይወት ለመከባከብ ሲል ለግ ራኝ ያልገበረው ሠራዊት ተጠራቅሞ በዙሪያቸው ስለሚገኝ በጠቅላላው በሚደረ ገው ጦርነት ሁሉ እየሸሹ ሲደርስባቸው ደግሞ ገትረው ይቋቋሙ ይሆናል ። አብዛ ኛው ጊዜ ድል ቢሆኑም ብዙ ሀብትና ሰው ቢማረክባቸውም አልፎ አልፎ የሚያሸ ንፉበት ምክንያት ይኸው መሆን አለበት ።

በአጠገባቸው የማይለያቸው ጦር እንዳላቸው ቢያውቁም በርሳቸው አንጻር ያለው ግራኝ አህመድ ያለው ጦር ከርሳቸው በማናቸውም ረገድ የበዛ መሆኑን በማ ወቅ አገሬውም ክርስቲያኑ በግዴታ እ[illegible] ፈላሻው በውዴታ የርሱ ተገዥና አገልጋይ መሆኑን ስለሚያውቁ ያላቸውን ጦር ራሳቸውን ለመጠበቂያ ወይም ለክፉ ቀን የመደቡት እንጂ በምንም ዓይነት ግራኝንም ገጥመው ለማጥቃት እንደ ማያስችላቸው ያውቁታል ።

አሁን ግን ግራኝ ባንድ አገር ሁለት ነገሥታት እንዳይኖር እርሳቸውን በኃ ብቻ ገመድ ስቦ በሥልጣኑ ውስጥ ለማግባት ፈትኖ እርሳቸው ደግሞ ይኸን ፈተና በወረወሩበት ጊዜ ያቀዘቀዘውን ጦርነት እንደገና ቀስቅሶ እነሆ ብዙ ጉዳት እንዳደረ ሰባቸው አንብበናል ። ጦርነቱ ከተዠመረ በተለይ ከሽምብራ ኰሬ ጦርነትና ከዓ ባይ ዳሩ አደጋ ወዲህ በዚህ በ፲፰፻፴፭ ዓ. ም. የደረሰውን የመሰለ አደጋና መከራ አልደረሰባቸውም ።

ስለዚህ ሸሽተው ሺሬ ተራራ በተቀመጡበት ሰዓት የበኵር ልጃቸው የፊቅ ጦር ሞት የሚናስ መማረክ እስከዚህ ዘመን ድረስ ያልተለዩዋቸው የጦር ሹማም ንት ዕልቂትና ምርኮ ትዕግሥታቸውን ጨርሶት ከትግሬም ትንሽ ተዋጊ አግኝ ተው አጠገባቸው ያለውንም የተረፈ ጦር ይዘው እንግዲህ ለምኑ ነው ሸሽት በሚል ተስፋ መቁረጥ ከተደበቁበት ተራራ ወርደው በድፍረትና በቆራጥነት አህ መድ ዲንን ተዋግተው ከመግደል ደርሰው ይሆናል ። በዚህ ዓይነት ቁርጠኝነትም ውጊያቸውን ሲቀጥሉ በመጨረሻ ያለ ዕረፍት ከአውራጃ ወደ አውራጃ እያሳደደ ይወጋቸው ከነበረው ከኤሚር ኡመር ጋር ተጋጥመው አቁስለውት ይሆናል ።

ነገር ግን ይህ ጨካኝ ጠላታቸው ኤሚር ኡመር ሊሞት የቻለው እንደ ታሪክ ነገሥቱ አጻጻፍ ባንድ ተራ ደሀ እጅ ነው ። ይኸን የመሰለውን ኃይለኛ ያገርና የን

ጉሡን ጠላት የገደለው ሰው ስሙ አገሩ ሥራው አልተገለጸም ። ጽሑፉ "አሐዱ ነዳይ ዘአልቦ ስም - ስም የሌለው አንድ ደሀ" ብሎት ስለሚያልፍ ስለርሱ በሙላ ምንም ሐተታ መስጠት አይቻልም ።

መቼም ደሀ ቢሆንም ማናቸውም ሰው መጠሪያ ስም እንዳለው የማይጠረጠር ነው ። ታሪክ ነገሥቱ የጻፈው ሰው ግን ወሬውን ጠይቆ ጽፎ ለትውልድ በማስተላለፍና ስሙ ጥር ሊያደርገው ሲችል ሳለ ስም የሌለው ደሀ ብሎታል ። በርሱ አነጋገር ስም የሌለው ማለቱ ከባላባት የማይወለድ ማዕርግና ወግ የሌለው ተራ ሰው ማለቱ ነው ።

ምናልባት የፊቅጦር ሞት የሚናስ መማረክ የተቀቡት ንጉሥ በዚህ በኡመር እጅ እንደዚህ አድርጎ መጠቃት የቆጨው ተራ ወታደር ወይም ገበሬ አለዚያም ነጋዴ የደሀ ልብስ ለብሶ ለማኝ ወይም ወሬ ነጋሪ መስሎ ገብቶ ሆዱን ተንደርድሮ በመሸርከት የልቡን ሠርቶ ይሆናል ። ወይም ዑመር በሺሬ አውራጃ ያሉትን የመጥበቢላን የደብረ ክርቤን አብያተ ክርስቲያናት ዘርፎ እያቃጠለ መነኮሳቱን በመፍጀቱ አጥብቆ የተናደደ ሕይወቱን ሠውቶ የመነኮሳቱን ደም ለመበቀል የቆረጠ ካህን ወይም መነኮሴ ይሆናል ።

ይህ ካህን ይሁን ወይም መሐይምን ከዚህ በፊት የደብረ ሊባኖስ የአትሮንስ ማርያም የነአባ ሳሙኤል ገዳም ሲቃጠሉ ብዙ ጊዜ መነኮሳቱ እንበልባሉ ውስጥ በፈቃዳቸው እየ[illegible]እየተቃጠሉ ጠላትን ምንም ሳይጎዱ መቅረታቸውን ከሞኝነት ቆጥሮ እርሱ ግን አዘንግቶ ገብቶ ባጭር ሾተል ሆዱን ዘርግቶት ይሆናል ። ይህ ሰው በዚህ ዓይነት ኤሚር ኡመርን ከሚስቱ ፊት በሾተል ቀዶ ከገደለ በኋላ ያምልጥ ወይም የኡመር ጭፍሮች ይግደሉት የተገለጸ ነገር የለም ።

## ምዕራፍ ፪

## የግሼን አምባ መበዝበዝ (፲፭፻፴፪ ዓ. ም. የካቲት ፫ ቀን) - ነገሥታቱ ያደለቡት ሀብት መልሶ አገሪቱን እንደአስጠቃ ።

ከኡመር ሞት በኋላ ታሪክ ነገሥቱ የአምባ ግሼንን መዘረፍ ያስከትላል ። አምባ ግሼን ጦርነቱ ከተገሠመረ እንሥቶ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሁለት ጊዜ እየተከበበ ባንደኛው ክቢ ጊዜ በ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. በኅዳር ወር ከባቢዎቹ የግራኝ የጦር አለቆች ገራድ ማታንና አውራይ ኡስማን ሞተው ገራድ አህሙሹ በነቢትወደድ ሠርጸ እጅ ተማርኮ ለንጉሡ ቀርቦ መገደሉን በምዕራፍ ፳፯ አንብበናል ።

በሁለተኛው ክቢ በ፲፭፻፳፭ ዓ. ም. ራሱ ግራኝ አህመድ ከዓረብ አገር አዳዲስ መድፍ አስመጥቶ ከቦ ሲዋጋ የታችኛውን ክፍል በጦር ኃይል ይዞ ብዙ ሰው ከፈጀ በኋላ የነገሥታቱ ልጆችና ብዙ ሀብት የሚገኝበትን የላይኛውን ክፍል መያዝ አቅቶት ክቢውን ትቶ ወደ ትግሬ ማምራቱን በምዕራፍ ፴፰ ተመልክተናል ።

እሁን ደግሞ በዚህ ዓመት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. በየካቲት ፫ ቀን ወዚር ሙጃሂድና አህመዱሽ ይኸንኑ የነገሥታት ልጆች መቀመጫ የሆነውን አምባ ግሼንን ወርረው እንደዘረፋት እንደዚህ ሲል ይገልጸል ። «በየካቲት ፲፬ ቀን ግሼን አምባ ነገሥት (የነገሥታቱ ልጆች መንደር) ተሸሮ ተዘረፈ ። በዚያም ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ የቀደሙት ነገሥታት ያከማቹት ብዙ ወርቅና የሐር ልብስ ተገኘ ። ሌላውን ሀብት ከእግዚአብሔር ከራሱ በቀር የሚያውቀው የለም ። በዚያን ጊዜ ወርቅ እንደ ድንጊያ የሐርም ልብስ እንደ ቅጠል ረከሰ ። ያንድ ወቄት ወርቅ ዋጋ ፴ አሞሌ ጨው የአንድ በሬም ዋጋ አንድ ወቄት ወርቅ ሆነ ። በተራራው የሚገኙት እስራኤሎች (1) በሰይፍ እየተመቱ ተገደሉ ። የቀሩትም ስለ ሃይማኖታቸው ወደ ባሕር እየተወረወሩ ሞቱ ። ይኸንንም ያደረጉት ወዚር ሙጃሂድና አምዱሽ (አህመዱሽ) ናቸው» (2) ።

በዚህ ዓይነት ሁለት ጊዜ ከዚህ በፊት ተሞክሮ ያልተደፈረው ይህ የግሼን አምባ በዚህ በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. በየካቲት ፫ ቀን በወዚር ሙጃሂድና በገራድ አህመዱሽ መሪነት በምን አኳኋን ተደፍሮ ለመውደቅና ለመዘረፍ እንደቻለ ታሪክ ነገሥቱ በተለመደ ቁጥብነቱ ሊዘረዝርልን አልቻለም ። የዚህ አምባ አወዳደቅ የመሣፍንቱ አሟሟት በዓረብ ፋቂህ እጅ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ በሁለቱ ባላጋራዎች መካከል የተደረገውን ውጊያ የተፈጸመውን ጀብዱ በዝርዝር እናገኘው ነበር ። ሁለት ጊዜ ከዚህ በፊት የግራኝን ጦር እየተከላከለ በመመለስ እስከዚህ የቆየው ግሼን አምባ የብዙ ሰው ደም ሳይፈስ የብዙ ሰው አጥንት ሳይከሰከስ በዋዛ እንዳልወደቀ ግልጽ ነው ።

ጀምስ ብሩስ ወዚር ሙጃሂድ አምባ ግሼንን ለመያዝ የቻለው ባንድ መሣፍንቱን ያገለግል በነበረ የእስላም ተወላጅ እርዳታ ነው ሲል ጠቅሷል (3) ። ብዙ ጊዜ ግራኝና ወገኖቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር በነበሩ እስላሞችም ወደነርሱ በገቡት ክርስቲያኖችም በስለላ በመንገድ አመራር ብዙ ጊዜ መጠቀማቸውን በየምዕራፉ አንብበናል ።

ስለዚህ በሐይቅ በመካነ እስጢፋኖስ ገዳም እንደተመለከትነው አንድ የእስላም ባላባትነት ያለው በግዞት ከመሳፍንቱ ጋር ሲኖር ምናልባት አሁን አታሎ ወደ እስላሞቹ ተደባልቆ በሚያውቅበት መንገድና ዘዴ እየመራ አምባውን እማስ ያዝ ደርሶ ይሆናል ። ወዚር ሙጃሂድና ገራድ አህመዱሽ አምባውን ሰብረው ገብ

(1) እስራኤላውያን የሚላቸው ከሰሎሞን ዘር የተወለዱትን የኢትዮጵያን የነገሥታት ልጆች ነው ።

(2) ወበይእቲ ወርኃ የካቲት እመ ፫ ተሰዕረ ወተበርበረ ግሼ አምባ ነገሥት ወተረክበ በሕየ ብዙኅ ወርቅ ወብዙኅ ልብሰ ሐሪር መዛግብተ ነገሥት ዘቀደምት ዘተዘግበ እም ይኩኖ አምላክ እስከ መንግሥቱ ለልብነ ድንግል ። ወለካልዓንሰ መዛግብት ዓልቦ ዘየአምር ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ። እሜሃ ኮነ ወርቅ ከመ እዕባን ወልብሰ ሐሪር ከመ ቆጽል ወኮነ ሤጠ ኅልቅ ፴ አሞሌ ፤ ወወቄት ለእሐዱ ብዕራይ ። ወለእስራኤልሰ እለ ነበሩ ሕየ ቀተልዎሙ በሰይፍ ወቦ እለ ተወርወሩ ውስተ ባሕር በሃይማኖቶሙ ። ወዘንተ ገብሩ ወዚር ሙጃሂድ ወአምዱሽ ታሪከ ነገሥት ገጽ 94 ።

(3) የጀምስ ብሩስ መጽሐፍ ፪ኛ ቮሊዩም ገጽ 182 - 183 ፤

ተው ግግሾቹን መሣፍንት በሰይፍ ሲፈጁ የቀሩት መሣፍንት በእስላሞቹ እጅ መሞቱንም መማረኩንም እየጠሉ በፈቃዳቸው ወደ ባሕር እየተወረወሩ መሞታቸው አስደናቂ ነው ። በዚህም ሥራቸው የደብረ ሊባኖስ ፤ የአትሮንስ ማርያም ገዳማት የተቃጠሉ ጊዜ ከነበልባሉ ውስጥ በፈቃዳቸው እየገቡ ከተቃጠሉት መነኮሳት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው ።

ይኸን እምባ በመሪነቱ ከቦ ከመጣል ያደረሰው ሙጃሂድ የአሊ ቤን አብደላ ልጅ ነው ። አንባቢ እንደሚያስታውሰው ሙጃሂድ የኢሚርነት ማዕርግ ይዞ በሽምብራ ኩሬ በባሌ በደዋሮ በይፋት በዋስል በፈጠጋር በሐይቅ የተዋጋበት ብዙ ነው ። ወደ መጨረሻም ማዕርጉ ከፍ እያለ ሄዶ ከኢሚርነት አልፎ የወዚርነት ማዕርግ እንደ አባስ አግኝቷል ።

ግራኝ ወደፊት ሲሞት በርሱ እግር ተተክቶ ሚስቱን ድል ወንበራን አግብቶ ዓፄ ገላውዴዎስን ከመግደል የሚደርሰው ኑር የወዚር ሙጃሂድ ልጅ ነው ።

ገዕዝኛው አምዱሽ ያለው የወዚር ሙጃሂድ ጓደኛ ትክክለኛ ዓረብኛ ስሙ አህመዱሽ ቤን ማንፉዝ ነው ። እርሱም በአባ እንድርያስ እጅ የተገደለው የኢሚር ማንፉዝ ልጅ የድል ወንበራ ወንድም ነው ። እርሱም በግራኝ አህመድ ወረራ እንደ ነሙጃሂድ ያልዋለበት ጦርነት በልክ ነው ።

የጊና አገሩን ገኸር ነገደ ኢየሱስን በአይፈርስ ጦርነት ላይ የገደለ እርሱ ነው ፤ በቤተ አም[illegible]ግራኝ አድብቶ በዋስል ንጉሡን ለመማረክ የደረሰለት በውጊያ ጀግንነቱን አሳይቷል ። ነገር ግን በዚህ በ፲፭፻፴፪ ዓመተ ምሕረት በርሱና በሙጃሂድ እጅ የወደቀውን ግሼን አምባን ከነገራድ ማታን ጋር በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. በከበበ ጊዜ ጓደኞቹ እነማታን እነአውራይ ኡስማን ሞተው አህሙሹ የተማረከ ጊዜ እርሱ ከሞትም ከምርኮም አምልጦ ወደ ግራኝ መምጣቱን በዚህም ግራኝ "ጓደኞችህን አደጋ ላይ ጥለህ ሸሸህ" በማለት ሊገድለው ፈልጎ በምልጃ መዳኑን በዚያው ምዕራፍ ላይ ያነበብነው ትዝ ይለናል ። ከዚያ ወዲህ በወዚር አዶሌ ውስጥ ሆኖ በባሌ እነአዝማች አዳሉ ተዋግተው የሞቱበትን ጦርነት ተካፍሏል ። በዛላህ ጦርነት የሻርቃህ (ሺርካ አሩሲ ?)ን አገረ ገኸር ሲሙን የገደለ እርሱ ነው በሠራዬ ወዚር አባስ የአዶሌን ገዳይ ተስፋ ልዑልን በመግደል የተበቀለለት አብሮ ተዋግቷል (1) ።

የሆነ ሆኖ እነሆ ፲፭ ዓመት ሙሉ የግራኝን ወረራ ፪ ጊዜ ተከላክሎ ለመመለስ የቻለው አምባ ግሼን ባሁኑ ጊዜ ወደቀ ። በላዩ ላይ ቊጥሩ የማይታወቀው የደለበ ሀብት ተበዘበዘ ። ታሪክ ነገሥቱን የጻፈው "የሀብቱ ቊጥር አይታወቅም" ቢል ለቃለ እጋኖ ያመጣው አይመስልም ።

የኢትዮጵያ ሀብታምነት ከጥንት ዠምሮ የታወቀ ነው ። ያገሩ ስፋት ከአሁኑ ቢበልጥ እንጂ አይጠብም ። ግራኝ እስከተነሣበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደ አውሮፓ መንግሥታት ባይሰለጥንም የቆየ ወግና ሥርዓት ያለው የደረጀና የተዘጋጀ በዚያን ዘመን አነጋገር ጨዋ እየተባሉ ዣን አሞራ ፤ ዣን ጸገና ፤ ጸር ሞጀት ፤ አዳል አምባ ፤ አዳል መብረቅ ፤ ድል ገጽ የሚባሉ ልዩ ልዩ የጦር ሠራዊት

(1) አረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 21 - 22 የማስታወሻ ቍ. 2 ።

ነገሥታቱ ስላሉዋቸው በምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ እንደልብ እየተስፋፉ ሀብ ታሙን አውራጃ ሁሉ እንዳስገበሩ ግልጽ ነው ። በዚያን ጊዜ በምሥራቅ በሰሜን በምዕራብ በኩል ካሉት ዓረቦችና ግብጾች በቀር በምዕራብ ደቡብና በምሥራቅ ደቡብ ያለው ዛሬ ኬንያ ውጋንዳ የሚባለው ሁሉ በመደዳው ምንም ሥልጣኔና የተ ደራጀ ጦር የሌለው ስለሆነ እነሱን በቀጥታ ቢቀር በነርሱ አካባቢ ያለውን ሁሉ ሳያስገብሩት አይቀሩም ።

ነገሥታቱ ወይም መሣፍንቱ ራሳቸው ወደ አውሮፓ ሄደው ወይም ሰው እየ ላኩ የፈረንሳዊን የኤስፓኝን በተለይም ወዳጅነት የወጡትን የፖርቱጋል ቤተ መን ግሥት ነገሥታቱ መሣፍንቱና መኳንንቱ የሚጠቀሙበትን አጹኛ ይኸውም ማለት የነዚያን የልብሳቸውን የጫማና የባርኔጣቸውን በጠቅላላው ጌጣጌጣቸውን ባይናቸው ዓይተው ከነርሱ እየተማሩ ቅጅ ወስደው ከፍ ባለ በሚያምር ደረጃ ራሳ ቸውንም አልጠቀሙበት የሕዝባቸውንም የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል አልጣሩበትም።

በዚህ በበረከተ ወርቅና ብር የውጭ አገር መምህራን እየተቀጠሩ መጥተው የአገራችን ሕዝብ የብረትና የመሣሪያ ሥራ ፤ የሕክምና ትምህርት ሌላውንም አውሮፓ ያፈራውን ልዩ ልዩ ጥበብ እያስተማሩ የሕዝቡን አእምሮና ሕይወት ያሻ ሽሉበት የሚል አሳብ አንድ አንድ ጊዜ የውጭን አገር ሥልጣኔና ኑሮ በስሙ ጥር ነገሥታቱና የሥራ ጓደኞቻቸው እንደሚመጣባቸው የታወቀ ነው ። ለፖር ቱጋል ንጉሥ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ባዬ ል[illegible] ድንግል ዘንድ ይህ ስሜት እንደነ በረ ተገንዝበናል ።

ነገር ግን በዚያ በመካከለኛው ዘመን ያለው የቆየው የሥጋዊና የመንፈሳዊ ልማድ የጉልተኝነቱና ነዋሪውን ብቻ ላለመልቀቅ ቤተ ክህነቱ የሚያደርገው ምርጫና ከፈረንጅ የመነጨውን ሥልጣኔ እንደዛሬ ለመከታተል መሪዎቹ ስለሚያ ግዳቸው ከቀረጥ ከእጅ መንሻ ከግብር የሚገኘው የወርቅ የልብስ የከብት ሀብት ሁሉ እንደዚሁ እየደለበ ይቀመጣል ። እንኳን ሕዝብን ለማስተማሪያና አገር ለማሰ ልጠኛ ነገሥታቱና መሣፍንቱየቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች በዚ በዚህ ሀብት ራሳቸው እንኳን ደህና አድርገው መጠቀምን አያውቁበትም ። በዚ ያን ጊዜ ልብሱም ጌጣጌጡም መብልና መጠጡም ሁሉም ገደብ አለው ። ከወርቅ በተሠራ ነገር ሊያጌጥ የተፈቀደለት በጣም የተወሰነ ነው ። ወርቅ ቢኖረው ባለው ወርቅ ፤ ሀብት ቢኖረው በሀብቱ እንደልቡ ሊያጌጥበትና ሊሽቀረቀርበት አይች ልም ።

ጦርነቱ ከተዠመረ አንሥቶ ከየገዳሙ ሲዘረፍ ያየነው አሁን ከአምባ ግሼን ሲዘረፍ ያነበብነውን ታሪክ ነገሥቱን የጻፈው "የቁጥሩን መጠን ከርሱ ክባለቤቱ ከእግዚአብሔር በቀር ማን ያውቀዋል" ካለ በኋላ ከዚሁ አያይዞ "ይህ ሀብት ከዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ድረስ (፲፪፻፷፪ - ፲፭፻፴፪ ዓ. ም.) የተከ ማቸ መሆኑን የገለጸው በዚህ ዘመን ያለፈው ጊዜ ፪፻፸ ዓመት ነው ። በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ በዙፋን የወጡት ነገሥታት ሁሉ ከግብር ከቀረጥ ከመታያ የሚያገኙ ትን በመጠኑ ተጠቅመው የቀረውን የወርቅና የልብስ ሀብት ለየገዳማቱ ለየአብ

ያተ ክርስቲያኑ ታድሎ የተረፈውን ብዙውን ወደነዚሁ አምባዎች እየላኩ በላይ በላዩ ማስቀመጥ ልማዳቸው ነበር ።

ባዬ ልብነ ድንግል ዘመን በ፲፭፻፲፪ ዓ. ም. መጥቶ በኢትዮጵያ ፮ ዓመት ቆይቶ የተመለሰው ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ሲመለስ ስለካህኑ ዮሐንስ (ዓጼ ልብነ ድንግል) አገር እውነተኛው ወሬ በሚል አርእስት በጻፈው መጽሐፉ ላይ «ካንድ ከጐጃም ግዛት ባንድ ዓመት ብቻ ፴፻ ወቄት ወርቅ ፤ እያንዳንዱ ከ፪ እስከ ፩ ወቄት ወርቅ የሚያወጣ ፫፻ ሥጋጃ የሚመሳሰሉ ቡልኮዎች ፤ ፴፻ ከጥጥ የተሠራ ልብስ ፤ ፫፻ በቅሎ ፫፻ ፈረስ በሰልፍ በንጉሡ ፊት እያለፈ መግባቱን ባይኑ ማየቱን ሲጽፍ ፤ ወርቁ ግን በገበታ (መሶብ) ውስጥ ተሸፍኖ ማለፉንና መጠኑ ፴፻ ወቄት መሆኑን ጠይቆ መረዳቱን ይገልጻል ። በዚህ ቀን አንዱ ቢትወደድ የጐጃ ምን ግዛት ግብር በጠቅላላው ሲያስገባ የማስገባቱና የማስረከቡ ሥነ ሥርዓት ፲ ሰዓት ፈጀ» ሲል የጻፈውን ከዚህ በፊት አንብበናል (1) ።

ከርሱ በፊት ባዬ እስክንድር ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፸ - ፲፬፻፹፯ ዓ. ም.) መጥቶ ፖርቱጋሎቹን በአስተርጓሚነት ያገለገላቸው ፒድሮ ደኮቪልሐኦ ስለ መንግሥቱ ሀብት ብዛት እየተደነቀ ለአልቫሬዝ ሲያጫውተው እንደዚህ ብሎታል ። «በያመቱ ብዙ ወርቅ ማስቀመጥ እንጂ ምንም ስለማይወስዱለት ባንዱ ዋሻ የተጠራቀመው ወርቅ ዓለምን ሊገዛ ይችላል» (2) ። ደ. ኮቪልሐኦ ይኸን የሚለው በቤተ እምሐራ ሲያልፉ በዘበኛ ሲጠበቅ ስላዩት ስለ አንዱ ዋሻ ሀብት እንጂ በየአውራጃው በየቤተ መንግሥቱ በየገዳማቱ በየአምባው ስለተቀመጠው ስለአገሪቱ ጠቅላላ የወርቅ ሀብት አይደለም ።

ራሳቸውም ዓጼ ልብነ ድንግል በነዚሁ በነአልቫሬዝና በዋናው መላክተኛ በሮድሪግ እጅ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤል እንደ አው. ቍጥር በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ «በአሁኑ ሰዓት የአረመኔዎችን አገር (3) ለመውረር መመካከር ይዘናል (4) ። ከኔ በኩል በማናቸውም ለዚህ ጉዳይ ባለኝ ኃይል ሁሉ ለመሥራት የተዘጋጀሁ ነኝ ። ካሁን ዠምሮ ሺ ጊዜ መቶ ሺ (100.000.000) የወርቅ ድራህም እሰጣለሁ» (5) ካሉ በኋላ ለልጁ ለዮሐንስ ፫ኛ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ደግሞ «እኔም በበኩሌ ሰውም ወርቅም እሰጣለሁ ። በኔ ዘንድ ይኸ ሁሉ (ሰውና ወርቅ) እንደ ባሕር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበረከተ ነው» ያሉትን ደግመን እናስታውሳለን ።

በዚህ ደብዳቤያቸው ንጉሠ ነገሥቱ የገለጡትንና አልቫሬዝ ከውስጥ አዋቂው ከደኮቪልሐኦ ሰምቶ የጻፈውን ስናነብ ባለፉት ዓመታት ቢዘረፍ ቢዘረፍ አላልቅ ያለው የመካነ ሥላሴ ፤ የአትሮንስ ማርያም ፤ የደቀ እስጢፋኖስ ሀብት ዓረብ ፋቂህ ጽፎ ያቆየልንን ስንመለከት የአገሪቱንና የመንግሥቱን ሀብት ብዛትና በበዛው

(1) Verdadeira infermacao F. Alvarez ምዕ. 118
(2) ,, ,, F. Alvarez ምዕ. 128
(3) የአረመኔ አገር የሚሉት ዓረብን ይሁን ወይም የአዳልን ግዛት ይሁን አይለይም ፤
(4) ምክሩ ከሮድሪግ ይመስላል ፤
(5) 5 ድራህም ጥንት ግሪኮች የሚገበያዩበት ገንዘብ ነው ።

ሀብት ግን አገሪቱ አለመጠቀሟን ስንረዳ በአገሪቱና በሕዝቡ ፋንታ አሁን ጠላት እየተጠቀመ አገሪቱን እየጐዳ ሲታይ ሁኔታው አሳዛኝም አስደናቂም ነው ።

በዚህ በዓፄ ልብነ ድንግል የመከራ ዘመን መጨረሻ በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. በየካቲት ፫ ቀን ይህ ታላቅ የነገሥታት አምባ ግሼን በወዚር ሙጃሂድና በአህመዱ ሸ ሲበዘበዝ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ በ፪፻፷ ዓመታት ውስጥ የነገሥታቱ የደለበው የወርቅና የሐር ልብስ ሀብት ወርቁም የሐሩም ልብስ ተዘርፎ እስላሞቹ እንደልባቸው ከተከፋፈሉ በኋላ "ወርቅ እንደ ደንጊያ የሐር ልብስ እንደ ቅጠል" መርከሱን ታሪከ ነገሥቱ በደንብ የገለጠውን የዓረቡ ጸሐፊም እንዳጸደቀው ባለፈው አንብበናል ።

መቼም በሀብት መጠቀምን አገር መጥቀምን ሕዝብን ማሠልጠን ያገርን ሀብት ለሕዝብ እየተነተኑ የማዳረሱን ጉዳይ ዛሬ በምናስበው የልማት መንገድ መሥራቱ እንኳን በርሳቸው ዘመን ከርሳቸውም ዘመን ወዲህ ከፈረንጅ ጋር ግንኙነት ለማድረግ የበለጠ ዕድል የነበራቸው ነገሥታት አልሆነላቸውም ። ኃላፊነቱም ያንዱ የንጉሥ ነገሥቱ ሳይሆን በጠቅላላው የድምሩ የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱ ባለሥልጣኖች ነው ። ምናልባት እነርሱን ደግሞ ከኃላፊነት የሚያስጥላቸው የዚያው ዘመን የሁሉም የግትርነት ጠባይና ልማድ ወይም ለሥልጣኔ የማይመቸው ራሱ ዘመኑና ያገሪቱ አቀማመጥ ይሆናል ። ይኸውም ማለት ወደቡ ሁሉ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ በዓረቦችና በግብፆች እጅ ኢትዮጵያ ከሠለጠነው ዓለም ጋር ፈጽማ በመለያየቷ ለማለት ነው ።

ያለዚያ ግን ዓፄ ልብነ ድንግል ከነገሡበት ጊዜ ከ፲፭፻ ዓ. ም. እንኳን ቢቀር ሥልጣን ከጨበጡበት ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ ግራኝ እስከ ተነሣበት እስከ ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ድረስ ባለው የአሥራ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለነዶም ሮድሪግ ያሳዩት የደጅ ማስጠናት የሥርዓትና የወጉን የመንፈሳዊውን ክርክርና አሳብ ተወት አድርገው እንደዚህ ከደለበው ሀብት እየከፈሉ ፖርቱጋልና አውሮፓ በጊዜው ማጠር ምክንያት እንኳ ቢርቃቸው ሕንድ ካሉት የፖርቱጋል ባለሥልጣኖች እየተላላኩ መድፍና የጦር መሣሪያ በጊዜው አሰብስበው የጦር ሠልፍና አተኳኮስ የሠይፍ አመታትና አመካከት የሚያስተምር አስመጥተው እንደ አሸዋ ከበረከተው ሕዝባቸው ወጣቱን አስተምረው ቢሆን ኖሮ እንደዚህ አድርጎ ግራኝ አህመድ በርሳቸውም በአገሪቱም ላይ እንደልቡ ባልተጫወተ ነበር ። እነዚያ ሁሉ የጦር አለቆችና ወታደሮች በደዋሮ በፈጠጋር በአይፈርስ በሽምብራ ኩሬ በዳሞት በዋስል በተምቤን በሺሬ በወገራና በሰሜን ደማቸው በዋዛና በከንቱ ባልፈሰሰ እነሱም ሲያልቁ ነዋሪው ሕዝብ ስለም እየተባለ እንደበግ ባልታረደ ነበር ።

እንኳን ለዝምድና የፈለጉዋቸው ክርስቲያኖቹ ፖርቱጋሎች ወርቅ በብዛት ከከፈሉት ግለኛው ዓረቡና ቱርኩ እንኳን ወታደር ለማሠልጠን የጦር መሣሪያ በሥውር አምጥቶ ለመሸጥ አይመለስም ነበር ። ነገር ግን በዋዛ በቸልታ ያሳለፉት የሰላም ጊዜ ሳይሠራበት በከንቱ ስለ አለፈ በአሁኑ ሰዓት ንጉሡም መሪዎቹም የደረሰባቸውን መራራ የመከራ ቀን በርግጥ ጸጸትም የግዴታ ትዕግሥትም በተደባለቀበት

ስሜት ውስጥ ተዉብጠው ከመሸከም በቀር ምንም ለማድረግ አይችሉም ። የጀግና ሙያ መገለጫው በመሣሪያ ነው ። መሣሪያ ከጐደለው ጀግናው መሣሪያ ባለው ፈሪ ሊማረክና እንደ ከብት ሊነዳ ይችላል ። ባሁን ጊዜ የደረሰው ይኸው ነው ።

ስለዚህ አባቶቻቸውና እነርሱ ሥራ አስፈትተው እነሱም ሳይጠቀሙ ሕዝቡንም ሳይጠቅሙ ያደለቡትን የወርቅና የልብስ ሀብት ግራኝ አህመድ በየጊዜው እየዘረፈ ወደ ዓረብ አገር እየላከ ዘመድና መሣሪያ ገዛበት ፤ ወታደር መለመለበት ፤ በዝርዝር እያደለ ተከትሎት የመጣውን የአዳሉን ፤ የሱማሌውን ፤ የዓረቡን ፤ የሕንዱን ፤ የፋርሱን ወታደርና ሹም አከበረበት ።

እስካሁን ድረስ እርሳቸውንም ጦራቸውንም እያበረረ የሚወጋበት የሚገድልበት የሚማርክበት አብዛኛው ከርሳቸው አገር ቤተ መንግሥትና ገዳም ወይም እምባ በተዘረፈ ሀብት የተገዛ መሣሪያና በተቀጠረ ወታደር ስለሆነ ሥራ ፈቶ የተቀመጠው የገዛ ሀብታቸው ተመልሶ ጠላት ሆኗቸዋል ከማለት በቀር ሌላ ትርጉም የለውም ። ለወደፊት መሪዎች ታላቅ ትምህርት የሚሆን በዚህ በግራኝ የጦርነት ታሪክ ውስጥ ሞልቷል ።

ታሪክ ነገሥቱ "ወርቅ እንደ ደንጊያ የሐር ልብስ እንደ ቅጠል ረከሰ" ብሎ ቃለ አጋኖ እየጨመረ የተናገረው በትክክል ወርቁም የደንጊያ ያህል የሐሩም ልብስ የዛፍ ቅጠል ያህል እንኳን ባይረክስ ያሁኑ ወርቅና የሐር ልብስ በብዛት በእስላሞቹ እጅ መገኘት ከቀድሞ ውድነቱ ጋር ሲያመዛዝኑት ሊያሰኝ ይችላል ። እላይ እንዳመለከትነው የዓረቡ ጸሐፊ ግራኝ በቤተ አምሐራ እነመካነ ሥላሴን ሲያዘርፍ ከርሞ ተዋጊው ሹምና ወታደር እስኪበቃው ጠግቦ የተረፈውን አስጭኖ ተመልሶ ወደ ደብረ ብርሃን (ቋጉለት) መጥቶ ከነወዚር አዶሌ የተገናኘ ጊዜ ሳልዘመቱት ለሄዱ ሹማምንትና ለወታደሩ ጥፍጥፍ ወርቅ የሐር ልብስ ለሁሉም እንደ ድርሻው አከፋፈለ ካለ በኋላ በእስላሞች ዘንድ ወርቅ ተትረፈረፈ ። ከእስላሞቹ ውስጥ አንዱ አንድ ነገር ሲያስፈልገው ወርቅ በጁ ይዘግንና ከገበያ ሄዶ ሸቀጥ ገዝቶ ይመለሳል ፤ አንዱ ወዳጁ ወዳንዱ ሄዶ ብር የሰጠው እንደሆነ "ይኸን የምትሰጠኝ ፩፻ ወይም ፪፻ ወቄት ወርቅ አጥተህ ነው ?" ብሎ መቆጣቱን "ያንድ በቅሎ ዋጋ አርባ ወቄት ወርቅ ሆነ" ያለውን መልሰን ስናስታውስ በዚህ በወርቅ አረካከስ አገላለጥ የዓረቡ ጸሐፊና የታሪክ ነገሥታችን ጸሐፊ በሙሉ ተስማምተዋል ።

## ምዕራፍ ፻፭

## በኢትዮጵያ የደረሱት ጦርነቶች — የግራኝ አህመድ ጽኑ ተዋጊነት — ያፄ ልብነ ድንግል ዕረፍት (፲፭፻፴፪ ዓ. ም. መስከረም ፭ ቀን)

ለኢትዮጵያ በታወቀው ታሪኳ ውስጥ ፭ ዋነኞች ጦርነቶች ገጥመዋታል ። አንደኛው የነጋሢን ዘሮች ማጥፋቷን አብያተ ክርስቲያናት ማቃጠሏን በጠቅላላው የም

ናውቀው በዘጠነኛው መቶ ዓመተ ምሕረት የደረሰው የፈላሻዪቱ የዮዲት ጦርነት፤ ፪ኛ ይህ በ፲፮ኛው መቶ ዓ.ም. የግራኝ አህመድ ጦርነት ፤ ፫ኛው በ፲፰፻፷፯ና በ፲፰፻፷፰ ዓ.ም. ከግብጾች ጋር በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. ከደርቡሾች ጋር ዓፄ ዮሐንስ ያደረጉት ጦርነት ፤ ፬ኛ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ ከጣልያኖች ጋር ያደረጉት የዓድዋ ጦርነት ፤ ፭ኛው በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ኢጣልያኖች የዓድዋን ድል ለመበቀል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ያደረጉት ወረራ ነው ። የቀረው ለምሳሌ ዓፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉት ጦርነት ያለበቂ ምክንያት የተደረገ ፤ ይኸውም ማለት በወረራና አገርን በመከላከል ሳይሆን የዜጎችን እሥራት ለማስፈታት ሲባል የተደረገ ጦርነት ነው ። የጐንደር ነገሥታት እነሠርፀ ድንግል ከምጥዋው ፓሻ ጋር በየጊዜው ያደረጉት መቆራቆስ ቀደም ብሎ እነዓፄ አምደ ጽዮን ከነሰብረዲን ጋር ያደረጉት ውጊያ ሁሉ ባንድ ወገን የውጊያው መጠን እንደ ዝቅተኛ ደረጃ በሌለው ወገን እንደ ውስጥ ጦርነት ሊቆጠር የሚችል ነው ።

ከነዚሁ ጦርነቶች መካከል ትክክለኛው ከውጭ መንግሥታት ጋር ውጊያ ሆኖ ብዙ ያገር ተወላጆች ደም የፈሰሰበት የግብጾችና የደርቡሾቹ ከዚያም ከኢጣልያ ጋር በሁለት የጊዜ ወቅት የተደረገው ታላላቅ ጦርነት ነው ። የዓድዋው ጦርነት በኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ከዚህ ጦርነት የተወለደው እልቂት መጠነኛ ቢሆንም የማይጨው ጦርነት ለኢጣልያኖች በማያኮራ አኳኋን በጋዝ መርዝ የተነሣ አሸናፊነቱን ኢጣልያ ካገኘች በኋላ አገሪቱን በያዘችበት በ፭ የወረራ ዓመቶች በግፍ የደረሰው እልቂት ከፍተኛ ነው ።


ISIC

ይሁን እንጂ ዝርዝሩን የማናውቀው የዮዲት እልቂት ወደጐን ይቀመጥና ግራኝ አህመድን የመሰለ ከባድና አስጨናቂ ባላጋራ ከርሱም በፊት ከርሱም በኋላ ለኢትዮጵያ እስካሁን ገጥሟት አያውቅም ። እንደ ወረራው ዘመን ርዝመት የእልቂቱ መጠን ከሌሎቹ ጦርነቶች ሁሉ ይበልጣል ። ንግርትን ተንተርሶ ከወላስሞቹ ሳይወለድ በድንገት የተነሣው አህመድ ቤን ኢብራሂም በጠባዩ ጨካኝና ቆራጥ በድል ላይ ድል ለማግኘት ግዛቱንና ሥልጣኑን ለማስፋፋት ሲል ለማንም ሕይወት የማይሳሳ ፤ ድል አድራጊነት ተከታትሎ ቢገጥመው የማይጠግብ ፤ የተትረፈረፈ የከብትና የልብስ የወርቅና የብር ሀብት ምርኮ ለግሉ የማያጓጓው ፤ ግዛትና ምርኮ በቃኝ የማይል ስለሆነ አንድ ትልቅ የጦርነት ድል ካገኘ በኋላ ሌላውን ወደፊት ለሚያገኘው ለሌላ ድል ከማሰብና የያዘውን ከማጥበቅ በቀር በቃኝ ልመለስ የማለት አሳብ በአእምሮው አይጸነስም ። ከአንድ ድል በኋላ በምክር ሰዓት ብዙ ጊዜ እንደተረዳነው ንጉሡን እናባርር ወታደሩን ዛሬውኑ እንበለው ባገሪቱ ነዋሪ ተቀማጭ ሆነን እንግዛ የሚል ወዳጁ ፤ እንግዲህ በቃን ምርኮዋችንን ይዘን ወደ አገራችን እንመለስ የሚለው ጠላቱ ነው ። በዚህ ጠባዩ ወደነእስክንድር ወደነናፖሌዎን ይጠጋል ከማለትም ይመስላል ቢባል ትክክለኛ ነው ።

ከራስ ደገልሃን ጋር የተዋጋ ጊዜ በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ፳፩ ዓመቱ ሲሆን አሁን ደግሞ የጋብቻው ፕላን ከከሸፈ በኋላ በአዲስ ኃይል ተቀስቅሶ ንጉሡን ያስዕረፍት በሚያሳድድበት በ፲፭፻፳፱ - ፴፩ ዓ. ም. ዕድሜው ወደ ፴፩ ዓመት ላይ ነው ። ነገር

ግን በ፲፭ና በ፲፮ ዓመት ዕድሜው መካከል በባደቆ ፣ በሽምብራ ኩሬ ፣ በአይፈርስ ጦርነት ጊዜ የጦር አመራሩ ዘዴውና እቅዱ የነገር አስተያየቱ ሁሉ በብዙ ጦርነት ላይ እንደዋለ የብዙ ዘመን የጦርነትና ያስተዳደር ልምድ ያለው መሪ ይመስላል ፡፡ የግሉንም ሳያስቀር በዚህ ጊዜ ከምርኮ በተገኘው ወርቅና ሀብት የጦር መሣሪያ ተገዝቶበት ተዋጊ ወታደር ተደራጅቶበት የተረፈውን የክርስቲያን ጦር እናባርር ነሡን እንማርክ ከማለት በቀር በዚህ የወጣትነት ዕድሜው የተገኘውን ወርቅና ብር ይገዤ አገሬ ገብቼ ልደሰትበት የሚል ስሜት አይመጣበትም ። እንደማናቸውም ጦርነት ወዳድ ወጣት ደግሞ በእልህና በንዴት በጦርነት መካከል ገብቶ ራሱም አይዋጋ ጦሩንም አያዋጋ ። ጦርነት የተዠመረበት ቦታ ለጠላት ምቹ መሆኑን ሲረዳ ወዲያው ሽሽት ያዛል ። በዙሪያው ሆነው ሰውነቱን የሚጠብቁ ምርጥ የሆኑ የተዋጊ ጋሻ ሻግሬዎች ስላሉት እነሱ በማናቸውም ጊዜ ከርሱ ሳይለዩ ይጠብቁታል ። የሚዋጋውም የሚያዋጋውም አስቀድሞ የጠላቱን መጠንና አቅም አመዛዝኖ ምቹውን ሥፍራ ገምቶ እንደ ነብር አድብቶ ይዋጋል እንጂ እንደ አንበሳ ፊት ለፊት ሄዶ ከጠላት ጋር የሚጋፈጥበት ጊዜ የለም ። ሲያስፈልግ ራሱ በቀጥታ ገብቶ ይዋጋል ፣ አንዳንድ ጊዜ ወታደሩ ከክርስቲያኖቹ ጋር ተደበላልቆ በሚዋጋበት ጊዜ እዳር ሆኖ እያመዛዘነ በዚህ መስመር ተዋጊ በዝቷል ፣ እገሌ ይቀነስና በላላበት በእገሌ ቦታ እገሌ ተጨምሮ ይዋጋ እያለ ከማስተናበር ጋር አንዳንድ ጊዜም ራሱ ወደባሰበት [illegible] ሄዶ በቀጥታ በዠግንነት ይዋጋል ። ባጉል ቦታ ማፈግፈግን እያዘዘ ባንድ ወገን ባስፈለገበት ቦታ ደግሞ ድፍረቱና ጭካኔው የዚያን ያህል ነው። ይኸን ሁሉ ድፍረቱን በባደቆ ፣ በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ፣ ዘዴውንና እልሆን ሲል መለስ እጥፍ እያለ በዘዴ መዋጋቱን በዋስል በአምባ ግሼን በበላያ ሻንቅሎች ጦርነት እንረዳዋለን ።

በዚህ ዓይነት እንደ ግራኝ አህመድ ያለ ለውጊያ ጊዜንና ምቹን ሥፍራ የመምረጥ ሀብት ያለው ድል የሚገኝበትን ዘዴ የሚያውቅ መሪ ከበታቹ ሆነው ጦር ለመምራት አገር ለማስተዳደር ለመዋጋት የጀግንነት መንፈስ ያላቸውን ለይቶ ለመረዳት ሰውን በችሎታው የመምረጥ ስጦታ ያለው አብዛኛው ጊዜ ድል የማድረጉና የገዥነት እድሉ ሰባ በመቶ የተረጋገጠ ነው ። ለራሱ ለአገዛዙ ለወረራው ይጠቅመኛል ብሎ የገመተውንና ዓይኑን ያሣረፈበትን ሹም በድለኸኛል ብሎ ለዘለቄታ ሊያርቀው አይፈልግም ። ይኸንንም የምንረዳው ግራኝ አህመድ በግብርና በምርኮ ሀብት የተነሣ ከሱልጣን ኡመር ዲን የተጣላ ጊዜ ስመ ጥሩው ተዋጊ ቀጭኑ አቡበከር ከሱልጣኑ ጋር ሆኖ በርሱ ላይ በቀጥታ ካደሙት ውስጥ ነበር ። በዚህ ምክንያት ቂም ይዞ ይኸን የመሰለውን ተዋጊ በግራቅ ፈንታ ከዚያ ወዲህ ባለሟሉና ከዋና የጦር አለቆቹ እንደ አንዱ በመቁጠር ስለአቀረበው ይኸው አቡበክር ከብዙ የክርስቲያን አለቆች ጋር ብቻ ለብቻ እየተጋጠመ ገድሎለታል ። በቃግማ (ቃጅማ) ተክለ ሃይማኖትን የማረከ ፣ በአይፈርስ ዘምቢልን በዝሆን ዱር ዓምደ ሚካኤልን የገደለ እርሱ ነው ። እሁንም በመጨረሻው ሹም ሽር አስፈሪውንና ሰፊውን የቤገምድርና የእግራ የላስታን የሰቆጣን የዋግን አገር ጠቅሎ በማ



የዓፄ ልብነ ድንግል ፀጽም ያረፈበት የአቡነ አረጋዊ ገዳም ባሁኑ ሁኔታ (ራሴ ያነሣሁት) ።

ISIC

ዛት የጋብቻውን የእምቢታ ቁጭት ለጌታው ለመወጣት ሲል ንጉሡን አድብቶ በዋግ ላይ የወጋና ጦራቸውን ያፈራረሰ ከቤተ ሰብና ከጦር አለቆች ብዙ የገደለ እርሱ ነው ።

ስለዚህ ምንም የእርዳታ ተስፋ ከውጭ ላላገኙት ከርሱም ተጋብተው አብሮ በፍቅር ለመኖር ላልፈለጉት ለኩሩውና ለተሸናፊው ላዔ ልብነ ድንግል ይኸን ከመሰለው ጠምዛዛና ጽኑ ባላጋራ ጋር ከሞት በቀር የሚገላግላቸው የለም ። ማሸነፍና ያለፈ ቁጭቱን ለመወጣት ላልታደለ መሪ ሕይወቱን ከዓለም ላይ ለመለየት ከመሞት በቀር ሌላ የዕረፍት ተስፋ የለውም ።

ስለዚህ ፲፫ ዓመታት ያህል በመከራ በስደት ከነቤተ ሰባቸው ከተንገላቱ በኋላ በመጨረሻም ከአራት ወንዶች ልጆች መካከል ፊቅጦር በጦርነት ከሞተ ሚናስም ከተማረከ ወዲህ በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. በመስከረም ፳ ቀን አርፈው የግራኝ ጦር ሊደርስበት በማይችለው በደብረ ዳሞ በአቡነ አረጋዊ ገዳም ተቀበሩ ። ሲሞቱ ዕድሜያቸው ፵፬ ዓመት ሲሆን የገዙበት ዘመን ፴፪ ዓመት ከ፵፰ ቀን ነው (1) ።

ዓፄ ልብነ ድንግል አባታቸው ዓፄ ናዖድ ከሞቱበት ከ፲፭፻ ከነሐሴ ፯ ቀን ዠምሮ እስከ ሞቱበት እስከ ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. መስከረም ፳ ቀን ያለው ዘመን የታሰበ እንደሆነ ፴፪ ዓመት ይሞላና ከነሐሴ ወር ላይ የሚተርፈው ፳፫ ቀን ከጳጉሜ ፭ ቀን ጋር ሲደመር ፳፰ ቀን ደግሞ ከመስከረም ፳ ቀን የተደመረ እንደሆነ ፵፰ ቀን ይሆናል ። ይህም ሲሆን የኔ ሃሳብ ከታሪክ ነገሥት ጸሐፊ ጋር የሚለያየው ባንድ ቀን ነው ። ነገር ግን የዓፄ ልብነ ድንግል ንግሥ አባታቸው በሞቱበት በነሐሴ ፯ ቀን ሳይሆን በማግሥቱ በነሐሴ ፰ ቀን ከዙፋን ላይ አውጥተዋቸው እንደሆነ ልክ እንደ ታሪክ ነገሥቱ የገዙበት ዘመን ፴፪ ዓመት ከ፵፯ ቀን ይሆናል ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ የዓፄ ልብነ ድንግል ሞት በውነት ዕረፍት እንጂ ሞት አይባልም ። "ግራኝ ልጅዎን ይዳሩልኝና እንታረቅ ብሎ የጠየቃቸው ጊዜ ልጄን ላንተ ሰጥቼ ባንተ እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅን እመርጣለሁ" ብለው የለመኑትን ምኞት እግዚአብሔር አልነሣቸውም ። የዚህን የከፋ ጠላታቸውን ፊት ሳያዩ ፤ በእርሱ እጅ ተማርከው ውርደቱንም መጉላላቱንም ሳይቀምሱ የነዘኑን ፤ የስደቱን ፤ የጦርነቱን መከራ በሙሉ ፈቃድ በሙሉ ሃይማኖት ጸንተው እንደተሸከሙ ሞቱ ። ይኸ መከራ በጊዜአቸው በመምጣቱ የተበደሉት ንጉሥ በግራኝ እጅ ሳይማረኩ እንደተመኙት በእግዚአብሔር እጅ ሲሞቱ ለርሳቸው እንደ ካሳ ይቆጠራል ። ግራኝ ልጅህን ለኔ ድረህ ካልተፋቀርህ በቀር የምታመልጥበት ሥፍራ የለም ያለው ስሕተት መሆኑን የሚረዳው በሕወታቸው መጨረሻ ደብረ ዳሞ ላይ ሲቀመጡ በዚህ ሥፍራ ለመድረስ አቅም ሲያንሰው ነው ። ከሞቱ በኋላ ደግሞ ፈጽመው ለዘለዓለም አምልጠውታል ። ዘያ፡ኛ ብልሀ ያልነው ግራኝ አህመድ እንደ

(1) ወእምድኅረዝ በመዋዕለ ማቴዎስ አዕረፈ ንጉሥነ ልብነ ድንግል አመ ፳ ለመስከረም ፡ ወሰከበ ምስለ አበዊሁ ። በዓመተ መንግሥቱ ፴ወ፪ቱ ። ወተቀብረ በዳሞ በደብረ አባ አረጋዊ ። ታሪክ ነገሥት ሬኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 332 ፤

ማናቸውም ሰው ዕውቀቱ ጉደሎ መሆኑን እንረዳለን ።

አሟሟታቸውንና የሞቱበትን ሥፍራ ታሪክ ነገሥቱ አይናገርም ። ጸሐፈ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሠራዬ ላይ መሞታቸውን ያምናሉ (1) ። በመጨረሻ የነበሩባቸው ሥፍራዎች በሺሬ እውራጃዎችና ታቦር በሚባለው ተራራ ነው ። ከዚያ ወርደው መዋጋታቸውን ተመልክተናል ። ዳሩ ግን በዚህ በመጨረሻዎቹ ዓመታት ከ፲፰፻፹፩ እስከ ፹፪ ዓ. ም. ከመቸውም የበለጠ የጦርነት ጽናት የልጆቻቸው የፊቅ ጦር ሞት ፤ የሚናስ መማረክ ከስደቱ ጋር ተጨማምሮ ኀዘንም ሕመምም አድሮባቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንዳሉት በሠራዬ ሞተው በደብረ ዳሞ ተቀብረው ይሆናል ወይም የግራኝ ማሳደድ በኃይል ማስጋቱን ሲያዩ ሊደርስበት ወደ ማይችለው በሕይወት ወደ ገዳሙ ወጥተው ቆይተው ሞተው ይሆናል ። ደብረ ዳሞ የሚገኘው በአጋሜ የአውራጃ ግዛት ውስጥ አዲግራት አጠገብ ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በ፲፰፻፶፫ ዓ. ም. ሲነግሡ ዕድሜያቸው ፲፭ ዓመት እንደነበረ ራሳቸው በደብዳቤ የገለጹትን አንብበናል ። ፲፭ዱን ዓመት ከነገሡበት ከ፲፰፻፶፫ ዓ. ም. ላይ ስንቀንስ የተወለዱበት ዓመት ፲፰፻፴፰ ዓ. ም. ሆኖ እናገኘዋለን ። አሁን ከሞቱበት ዓመተ ምሀረት ከ፲፰፻፹፪ ዓ. ም. ላይ ይኸንኑ የተወለዱበትን ዓመተ ምሀረት ስንቀንስ ሙሉ ዕድሜያቸው ፵፫ ዓመት ከ፵፪ ወይም ከ፵፫ ቀን ይሆናል ማለት ነው ።

ISIC

እነሆ ታሪኩ እንደሚያመለክተን በሞቱበት ሰዓት በኢትዮጵያ ግዛታቸው ከ፫ቱ እጅ በበለጠው ላይ የግራኝ ሥልጣን ተሰማርቷል ። የእርሳቸው የጦር ሠራዊት ግማሹን ሞት ግማሹን ምርኮ አገባዶታል ፤ ግማሹም ተስፋ በመቁረጥ ክልቡም ባይሆን በግዱ ለትዳሩና ለመሬቱ ሲል ወደ ግራኝና ወደ ሹማምንቱ እየገባ ለጊዜው ተስማምቶ መቀመጡ የታወቀ ነው ። ስለዚህ በሞቱበት ሰዓት በተለይ ከነኡመር ጋር ከተዋጉ ወዲህ ከርሳቸው ጋር የነበረው ጦር በጣም ትንሽ መሆን አለበት ። ከልጆቻቸው የበኵሩ ፊቅጦር በደዋሮ ሲዋጋ መሞቱን እንደተመለከትን ሁለተኛው ልጃቸው ሚናስ ከተማረከ በኋላ ወደ ዓረብ አገር በተለይ ለዘቢዱ ፓሻ ተልኳል ። አንደኛው ልጃቸው ያዕቆብ ወዴት እንደሚገኝ በትክክል አይታወቅም፤ አንዳንድ ጽሑፍ ዓፄ ልብነ ድንግል ሸዋን ለቀው ወደትግሬ ሲሄዱ መንዝ ላይ ትተውት ሄዱ ይላል ። እንግዴህ አሁን ዓፄ ልብነ ድንግል ከሞቱ በኋላ ምናልባት ባሁኑ ሰዓት ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ገላውዴዎስ ብቻ ይኖር ይሆናል ። ነገር ግን የግራኝ ጦር በሚያስፈራበት ሰዓት ብዙ ጊዜ ገላውዴዎስ ከመንገሣቸው በፊት ያለውን ጊዜያቸውን በስሜን ማሳለፋቸውን ወደፊት እናነባለን ።

ግራኝ አህመድ "ልጅህን ስጠኝና እንዛመድ ያለዚያ የምታመልጥበት ሥፍራ የለህም" ብሎ ላፄ ልብነ ድንግል ልኮባቸው "ላንተ ሃይማኖት ለሌለው አልሰጥም . . . . . ." ብለው ከመለሱ ወዲህ በአዲስ ኃይል ግራኝና ሹማምንቱ እነአሚር ኡመር ተቀስቅሰው ንጉሡን በሰለዋ ፥ በጸለምት በሺሬ እያሳደዱ ለመያዝ የተ

(1) ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 33 ፤

ቻላቸውን አድርገዋል ። የቀረውም አገር ለግራኝ የገበረና በግራኝና በጦሩ ጥብቅ መቈጣጠር ውስጥ በመሆኑ እርሳቸውን የማይቀበል ስለሆነ በሌላውም ወረዳ እርሱ የማይደርስበት ስለሌለ ዳልሜይዳ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ ኡመር በሰለዋና በጸለምት ከወጋቸው ወዲህ እርሳቸውም የሄዱት እርሱም በደስታ ተቀ ብሎ ያስተናገዳቸው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ የሚባለው መሆኑን ያረጋግጣል (1) ።

ስለዚህ እንደ ዳልሜይዳ አጻጻፍ ንጉሡ ከነቤተ ሰባቸው እላይ ያሉት ገመድ ቁልቁል ካልሰደዱ በቀር እታች ያለ ሰው በፍጹም ሊወጣበት ወደማይችለው ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ ሄደው ትንሽ ጊዜ እንዳረፉ በዚያው ሳሉ ሞተው በደብረ ዳሞ የአክሱሙ ንጉሥ ዓፄ ገብረ መስቀል ባሠራው በእቡን አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ገዳም ተቀበሩ ። ፲፫ ዓመት ሙሉ በጦርነትና በስደት ሲኖሩ በዚህም ረዥም ዘመን ሲመቻቸው እየተዋጉ ሳይመቻቸው ካገር ወዳገር እየሸሹ እንደኖሩ የጠላታቸውን መውደቅ ለማየት ፪ ዓመት ሲቀራቸው እርሳቸው ቀድመው ሞቱ ። ነገር ግን ከ፲፫ ዓመት ዠምሮ እንደ አባቶቻቸው ተድላና ደስታ ሳያዩ የሞቀ ቤተ መንግሥታቸ ውን ትተው በዱር በገደል ዘወትር ከመሰደድ ዘወትርም ግራኝ እዚህ ድረስ መጣ እንሽሽ እገሌ የሚባለው ሹማችን ሞተ ፤ እገሌ ደግሞ ተማረከ ፤ እገሌ ወደ ግራኝ ገብቶ ሰልሞ እኛን ወጋ የሚባለውን አሰልቺና ተስፋ አስቆራጭ የሮሮ ድምጽ ከመ ስማት ያለዕድሚያቸው ቢሆንም ሞት ለእርሳቸው እንደ ትልቅ እረፍት የሚቆጠር መሆን አለበት ።

ISIC

የዘመኑን ፖለቲካ የዚህን ዘመን የቱርክን መንግሥት ገናንነት በውስጡ ያሉት ዓረቦች ለግራኝ እህመድ የሚሰጡትን የእርዳታ መጠን ለውጊያ እየተጠራ ቀሙ ከውጭ የመጡትን የግራኝን የእመራርና የእወጋግ ችሎት መረዳት ያዳገታ ቸው አንዳንድ ሰዎች ጦር አውርድልን ብለው ስለተሳሉ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ግራኝን አመጣባቸው ብለው እንደጻፉት ሁሉ በዚሁ ሳቢያም አንዳንድ የፈረንጅ አገር ጸሐፊዎች ሉዶልፍ ፤ ዳልሜይዳ ፤ በቅምጥልነት አድገው ወይም ወደ ተድላ ደስታ አዘንብለው በግራኝ ጦርነት ፊት የሚገባቸውን የወንድነት ሥራና የመሪ ነት ሞያ አልፈጸሙም ወደ ማለት አዘንብለዋል ። በዚህ ዓለም ሰው ሁሉ ምኞቱን በዋዛ አይፈጽምም ። በሰውና በአገር ላይ መከራ ሲመጣ እውነትም ሐሰትም ቢሆን አንዳንድ ምክንያት መፍጠር የተለመደ ነገር ስለሆነ ፲፫ ዓመት ሙሉ መከ ራና ስደት ተሸክመው ሲዋጉ ሲያዋጉ በኖሩት ባፄ ልብነ ድንግል ላይ የውጭ አገ ርም ያገራችንም ጸሐፊዎች ሁላችንም መላ በመቀላቀል ብዙ ምክንያት ሰንዝረ ናል ።

ነገር ግን እውነተኛውን ታሪክ የተመለከትን እንደሆነ ዓፄ ልብነ ድንግል ጀግንነቱ መጠነኛ የሆነ ያንድ አገር ንጉሥ ሊፈጽም የሚገባውን የመሪነት ሞያ ፈጽመዋል ። ገና እሙሉ ሰውነት ሳይደርሱ ባፄ በዕደ ማርያምና ባፄ ናዖድ ጊዜ አገር እየዘረፈ ቤተ ክርስቲያን እያቃጠለ ምርኮ እየማረከ ያስቸገረውን ኃይለኛ ውን የግራኝን የሚስቱን አባት ኤሚር ማኀፉድን በራሳቸው መሪነት አባ ገብረ እንድርያስ እንደገደሉት እንብበናል ። ግራኝም ጦርነቱን በዠመረበት ጊዜ ሁሉ

ራሳቸው የዘመቱበት ሥፍራ ተነቧል ። ከዚሁ ዋና ውጊያ ሆኖ የሁለቱ ወገኖች የአሸናፊነት ዕድል ለተለየበት ለሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዋናው አዝማች እርሳቸው ነበሩ ።

ከመዠመሪያው ጊዜ በንቀት ወይም በችልታ ምክንያት ሙሉ ጥንቃቄና በቂ ድርጅት አለመደረጉም ጥርጥር የለውም ። ደግሞ በዚህ ላይ እንደግራኝ በየጦሩ ግንባር እየተገኙ ጦርጦራ ́መሪ ሆነው መንገድና ሥፍራ እየሰለሉ ጦር እየተነተኑ የጦርነቱን ሁኔታ በዝርዝር እየተቆጣጠሩ ራሳቸው በቀጥታ አለመምራታቸው አይካድም ።

በዚህ ላይ ልንመለከት የሚገባው ግራኝ ከዓባይ ገንንነት ከተራ ሰውነት የተነሣ የጦር አለቃ ሲሆን እርሳቸው እንደዘመኑ ልማድ በጳጳስ ተቀብተው ከንጉሠ ነገሥት አባታቸው ዘውድንና ዙፋንን የወረሱ ራሳቸው ንጉሠ ነገሥት ስለሆኑ በክብር ታጅበው መዋጋትና ማዋጋት እንጂ በየሥፍራው ወዲያና ወዲህ እየሮጡ የጦርነቱን እርምጃ ማስተናበር ያሉበት የማዕርግ ሥፍራ አይፈቅድላቸውም ። እርሳቸውም ቢፈቅዱ መኳንንቶቻቸው "ሺ አውል ከሚሞት ሺ ይሙት" በሚባለው ፍልስፍና እየተመሩ እንደሚከለክሏቸው ጥርጥር የለውም ። ባለፈው እንዳነበብነው ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ወዲህ የሐረሩ ሡልጣን ወደባሌ ድረስ መጣ ማለትን ሰምተው እኔ ራሴ ሄጄ እዋጋለሁ ቢሉ ራስ ወሰን ሰገድ እኔ ነኝ እንጂ እርስዎ አይሄዱም ብሎ በምክር እንደከለከላቸው እናስታውሳለን ። ሹማምንቱም የንጉሡን ሕይወት ለመጠበቅ የሚገደዱት ንጉሡ ሲሞቱ ምንም እንኳን ልጁን ለማንገሥ የሚቻል መሆኑ ቢታወቅ አገርና ሕዝብ ያወቀው ንጉሥ ሲሞት በተለይ በዚህ ጦርነት ሰዓት የሕዝብን ልብ አላልቶ የጠላትን መንፈስ ለማጠንከር እንደሚችል ተገንዝበው ነው ።

በዚህ ምክንያት በአጠገባቸው ባሉት መኳንንቶቻቸው እየተረዱና እየተመከሩ በተመቸበት ቦታ እየተዋጉ በማይመችበት ጊዜ እየሸሹ ብዙ ዘመን ካሳለፉ በኋላ እርሳቸው ግራኝን መመለስ ግራኝም እርሳቸውን ጨርሶ ማጥፋት ወይም መማረክ የማይሆንለት ሆኖ በመጨረሻ ጋብቻ እስከመጠየቅ መድረሱንና የርሳቸውን እምቢታ አንብበናል ። ደስታውንና ተድላውን ብቻ የሚወድ ቀብራራ ንጉሠ ነገሥት ቢሆን ኖሮ ልጅህን ዳርልኝና እንዛመድ ብሎ አንድ ጊዜ የሰጠው አሸናፊ ሰላማዊ እጁን ሲዘረጋለት በደስታ ተቀብሎ ውርደት ያለበትን ደስታ በዘመኑ ለመቀበል በሞከረ ነበር ። እርሳቸው ግን ላንተ ሃይማኖት ለሌለው ልጄን ሰጥቼ ደስ ከሚለኝ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅንና መሞትን እመርጣለሁ ብለው ሲመልሱ ምንም እንኳን ግራኝ በእግዚአብሔር የሚያምን እስላም እንጂ ሃይማኖት የሌለው አረመኔ አለመሆኑን ብናውቅም አንድ በጦር የተሸነፈ ኅሊናው ግን ያልተሸነፈ የተከበረ መሪ የሚሰጠው መልስ በመሆኑ ብቻ እርሳቸውን በታሪክ ፊት ለማክበር እንገደዳለን ። ስለዚህ እኚህ ንጉሥ በጦር መሪነት ችሎታ ዝቅ ብለው ቢታዩ በሞራል ደግሞ በጣም ከፍ ብለው ይገኛሉ ።

ይህ ሁሉ ተጠቃሎ ዓፄ ልብነ ድንግል እንደ ዓፄ ዓምደ ጽዮን ወይም እንደ

ቅርቡ እንደ ዓፄ ቴዎድሮስ ንቁ አርበኛ ግምባሩ የማይታጠፍ ዝግና አለመሆናቸ ውን ሳንዘነጋ አርበኝነታቸውና ተዋጊነታቸው የባሕርይ ሆኖ የተመጠነ በቀረው የንጉሠ ነገሥትነትና የመሪነታቸውን ተግባር በሃይማኖት በትዕግሥት በጽናት ተሸከመው እፍጻሜ ያደረሱ የርሳቸውን የተከታያቸውንም የነጋሢ ክብር ሳያዋ ርዱ ከዚህ ዓለም ድካም ይልቁንም እንደ ዕድል ባባቶቻቸው ጊዜ ሳይሆን በእርሳ ቸው ጊዜ ከደረሰው የረኸርም ዘመን መከራና ስደት አልፈው እሚሟታቸውን ያሳ መሩ ከወታደርነት ይልቅ ወደ መንፈሳዊነትና ወደ ቀለም ሰውነት በጠባይ ያዘነ በሉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው ። ይኸን ሁኔታ የአልቫሬጽ መጽሐፍ እጽድቆታል ። ታሪከ ነገሥቱም "የገላውዴዎስ አባት (ልብነ ድንግል) የመንፈሳውያንን መጻሕ ፍት ሕጋቸውን ውስጣቸውንም ላያቸውንም መርምረው ያወቁ ናቸው" በማለት በእርበኝነት ሳይሆን በቀለም ሰውነት ረገድ ያላቸውን ዝንባሌ አመልክቷል (፩) ።

ነገሥታት በዙፋን እየተከታተሉ በሚገዙበት ጊዜ ሥጋዊነትና መንፈሳዊ ነት ወይም ክፋትና ደግነት የተበረዘባቸው በደስታና በሰላም ከጎዘን ጋር በተቀላ ቀለ ኑሮ ሕይወታቸውን ከአሳለፉ በኋላ እንደ አጋጣሚ ነጋሢው ደግም ቢሆን ክፉ እንዳሁኑ እንዳፄ ልብነ ድንግል ባንደኛው ንጉሥ ላይ እንዳጋጣሚ የጦርነትና የብ ጥብጥ ጊዜ ይደርሳል ። ይኸም ከክፋቱ የተነሣ ሳይሆን በዕድሉ ወይም ባጋጣሚ በርሱ ጊዜ የሚደርሰውን የዚያን ዘመን ወይም ከዚያ ወዲህ የተነሣ ተቺ ትክክለኛ ውን ምክንያት መረዳት ያቃተው ሁሉ ባንድ ንጉሥ ላይ ጦርነት ሲነሣ የጦርነቱን ምክንያት በመመራመር ፈንታ በንጉሡ ክፋት ወይም ቀብራራነት እንደተነሣ ፤ ሰላም የሆነም እንደሆነ የሰላሙን ጊዜ ንጉሡ በደግነቱ ምክንያት እንዳመጣው ይቆጥሩለታል ።

የፈረንሳዊ ንጉሥ ፲፮ኛ ሉዊ የአባቱን የ፲፭ኛውን ይልቁንም የቅድመ እያ ቱን የሉዊ ፲፬ኛውን ያህል በቤተ መንግሥቱ ተድላና ደስታ አላየም ። በርሱም ዘመን ከቀድሞው የበለጠ ሕዝቡ ግፍና በደል አልገጠመውም ። ነገር ግን እርሱ ከነዚያ ያነሰ ተድላና ደስታ አይቶ በእነዚያ ላይ ያልደረሰው ሁከትና ሽብር ተጠ ቃሎ በርሱ ላይ ደርሶ በሕዝብ እጅ እመገደል አደረሰው ። በዚህ ምክንያት ወደ መገደያው ቦታ ሲደርስ አጭር ቃል ለመናገር ገዳዮቹን አስፈቅዶ «ዛሬ የምታፈ ሱት የንጹሕ ሰው ደም ግፉ በፈረንሳዊ ላይ እንዳይደርስባት ተስፋ አደርጋለሁ» የሚል ቃል ወርውሮ ተገደለ ።

ዓፄ ልብነ ድንግልም እግዚአብሔርን በመፍራትና በደግነት ከአባቶቻቸው ከነናዖድ ከነበዕደ ማርያም አያንሱም ። በመካከሉም አንዳንድ የማይገባ እንደ ግፍ ያለ ሠርተው እንደሆነ ግፉ ከአባቶቻቸው አይበልጥም ። ተድላና ደስታውም አባ ቶቻቸው ካገኙት የበለጠ አልነበረም ። ነገር ግን የግራኝ አህመድ አነሣሥና የቱ ርክ እርዳታ ባባቶቻቸው ጊዜ ሳይሆን እንደቀጠሮ በርሳቸው ጊዜ ስለደረሰ የርሳቸ ውን ዘመን ሁከትና መከራ ጦርነትና ስደት ሊከበው ቻለ ። ሁሉም አጋጣሚና ዕድል ነው ከማለት በቀር ሌላ ትርጉም የለውም ።

(፩) አቡሁኒ (የገላውዴዎስ አባት) ኮነ ግእዛረ አፍአሆሙ ወውሳጤሆሙ ለመጻሕፍት ሕግ መንፈ ሳውያን ታሪከ ነገሥት ገጽ 97

ISIC

# ፫ኛ ክፍል

# የዓፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት

## ምዕራፍ ፻፪

### ዓፄ ገላውዴዎስ ዕድገትና ንግሥ ፲፭፻፲፭ - ፲፭፻፴፫ ዓ. ም.

ዓፄ ልብነ ድንግል ወንዶች ልጆች ፊቅጦር ፣ ገላውዴዎስ ፣ ሚናስና ያዕቆብ መሆናቸውን መጻሕፍት ሁሉ ተስማምተዋል ። የነዚህ ሁሉ የመጠሪያ ስማቸው የመዝመሪያዎቹን አንጾኪያ ፣ ተወልደው አድገው በኋላ በክርስቲያንነታቸው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ስለ ክርስቶስ አምላክነት መስክረው በግብፅ አገር በሞቱት በቅዱሳን ሰማዕታት በፊቅጦርና በገላውዴዎስ ስም የመጨረሻዎቹ በእስራኤል ንጉሥ በሚናስና በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል የነገድ አባት በያዕቆብ ስም ተሰይመዋል ። ይኸን የመሳሰለው ከዚህ በፊት ሐዋርያትና ሰማዕታት ይጠሩበት በነበረ ስም አብዛኛው ጊዜ ነገሥታትና ልጆቻቸው ወይም ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት እንጂ ተራ ምዕመንና መኳንንት እምብዛም አይጠሩበትም ። ይኸውም ታውቆ ሕዝቡና መኳንንቱ በይሉኝታ ጭምር ሥያሜውን የሚርቁት ነው እንጂ በሕግ ለነዚያ ብቻ ተወስኖ ለነዚህ የተ[ከ]ለከለ ሆኖ አይደለም ።

ከነዚህ ከአራቱ የፊቅጦር የበኩር ልጅነት "የበሀር ልጁ ሞተ" የሚለው የታሪከ ነገሥት ዓረፍተ ነገር አረጋግጦአልና ክርክር የለበትም (1) ። እንደሚመስለውም ከፊቅጦር ፣ ገላውዴዎስ ፣ ሚናስ ፣ ያዕቆብ ተከታትለው የተወለዱ ይመስላል ። አንዳንድ ያገራችን ጸሐፊዎች ከነዚህም የታወቁት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ በዋዜማ መጽሐፋቸው ፣ ልብነ ድንግል ለታላቁ ልጃቸው ልብሰ መንግሥት ሰጥተው በሸዋ ትተውት እንደሄዱ ከመግለጽ ጋር ያዕቆብን ታላቅ አድርገውታል (2) ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በዳግማዊ ምኒልክ ዜና መዋዕል ውስጥ ያዕቆብን ታናሽ አድርገውታል (3) ።

በእውነትም ያዕቆብ ታላቅ ቢሆን ኖሮ ፣ በዚህም ላይ አባቱ በሕይወታቸው ሳሉ ልብሰ መንግሥታቸውን የሰጡት ከሆነ ፣ ካልታሠረ ፣ በማይድን በሽታ ካልተያዘ ፣ ወይም ካልሞተ በቀር ከአባቱ ቀጥሎ ለመንገሥ ምንም የሚከለክለው ነገር አልነበረም ። ያዕቆብ በዚህ ጊዜ በሕይወት ኖሮ የሞተው ፣ ዓፄ ገላውዴዎስ ከነገሡ ተዋግተው ሲሞቱ አንድ ዓመት ሲቀራቸው በ፲፭፻፶ ዓ. ም. ነው (4) ። ስለዚህ ደን

(1) ወሞተ ወልዱ ዘበኵሩ ታሪከ ነገሥት ገጽ 93
(2) ዋዜማ ምዕራፍ 16 ገጽ 53
(3) ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕራፍ 10 ገጽ 34
(4) Liber Axum - K. Conti-Rossini Corpusco ያሳተመው ገጽ 70 ። Chronique de Galawdewos-W. El. Gonzelman chap. LXXXVII ገጽ 187

በኛው ታሪከ ነገሥት ፊቅጦርን የበኵር ልጅ ስላደረገው ያዕቆብ ታላቅና የመዠመሪያው ልጅ አለመሆኑ ታውቋል ማለት ነው ።

እንግዲህ በሕይወት ያሉት ያፄ ልብነ ድንግል ልጆች ሦስት ሲሆኑ ፤ ከሦስቱ አንዱ ሚናስ ፤ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. በተደረገው ጦርነት ተማርኮ ለዘቢድ ባሻ ተልኳል ። ያልተጣራና መሠረት ያልያዘው አንዳንድ ያገራችን ጽሑፍ ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ዓፄ ገላውዴዎስ ተማክረው ሚናስን የነፍጥ መያዣ አድርገው ለፖርቱጊዝ መንግሥት ላኩት ብሎ ይገኛል ። ሌላውም ወደ ሮማ ተላከ ይላል ። ከዚሁ እያይዞ ኑር መሐመድ የተነሣ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ጦር ላኩልን ብለው ቢልኩ ፤ የፖርቱጋል መንግሥት ሚናስን ወደ ካቶሊክነት አስገብቶ በካቶሊክነት ቀብቶ እንግሦ ጳጳስ ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ ላከው ብሎ እውነት ባልሆነ መንገድ አስፋፍቶ ይጽፋል ።

ሚናስ በግራኝ አህመድ እጅ ከተማረከ በኋላ በምንም አኳኋን አምልጦ ወደ እናቱና ወደ ወንድሙ ተመልሶ ወደ ፖርቱጋልም ወደ ሮማም የነፍጥ መያዣ ሆኖ አልተላከም ። ግራኝ እንደማረከው በቀጥታ ወደ ዓረብ አገር ለዘቢድ ባሻ ልኮታል ። ወደርሱም የላከበት ምክንያት የቱርክ መንግሥት ከ፲፭፻፲ ዓ. ም. ዠምሮ ግብፅን ፤ የዓረብን አገር ሁሉ ከወረረ በኋላ በሌላው ግዛቱ እንደሚያደርገው በግብጽና በዘቢድ አንዳንድ ባሻዎች እየሾመ ይልክ ነበር ። ከግብጹ ይልቅ የዘቢዱ ባሻ ከግራኝ ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው ። ስለዚህ ግራኝ ከወዲህ ከኢትዮጵያ በዘረፋ ያገኘውን የወርቅና የልብስ ሀብት ሲልክለት ፤ የዘቢድ ባሻ ደግሞ ከዚያ የጦር መሣሪያ የያዘ ወታደር እየመለመለ ይልክለታል ። በተለይ ባሁኑ ሰዓት በዘቢድ የሚቀመጠው ባሻ ራሱ የቱርክ ተወላጅ በሌሎቹ በአደንና በሐድራሞት በመስታን ላሉት የዓረብ ሡልጣኖችና ያገር ባለባቶች እንደ በላይ ሆኖ ያስተዳድራል (1)።

ስለዚህ የበለጠ የጦር መሣሪያና ወታደር ለማግኘት የዓፄ ልብነ ድንግልን ጦር በያለበት ሊያሸንፍ የቻለበት ዕርዳታ እንዳይቋረጥበት ሲል እንደ መያዣ ወይም እንደ መታያ አድርጎ ለቱርኩ ተወላጅ ለዘቢድ ባሻ ሚናስን የላከው ራሱ ግራኝ አህመድ መሆኑ አይጠረጠርም ። ማስረጃውም ወደፊት ይነበባል ።

በዚህ ዓይነት ዓፄ ልብነ ድንግል በሞቱበት በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ባገር ተርፈው የሚገኙት ገላውዴዎስና ያዕቆብ ስለሆኑ ፤ገላውዴዎስም ታላቅ ስለሆኑ ከአባታቸው ከዓፄ ልብነ ድንግል ቀጥሎ ነገሡ ። ያገራችን ታሪከ ነገሥት የቀሩትን የነገሥታት ልጆች አቤቶ(አቤቶሁን)እያለ የቅጽል የማዕርግ ስም እየሰጠ ሲጠራቸው ፤ ገላውዴዎስን ግን ገላውዴዎስ ነው የሚላቸው ። ግን በሶርያና በዕብራይስጥ ቋንቋ ጌታው ወይም ምሑሩ ተብሎ ለመንፈሳዊና ለደገኛ ሰዎች የሚሰጥ የቅጽል ስም ነው ። አለቃ ኪዳነ ወልድ ፤ እግዚእ ጌታ ተብሎ ለአምላክ የሚሰጥ ቅጽል ሆኖ ለሰውም የጌታ ጌታዬ ተብሎ የሚሰጥ መሆኑን አረጋግጠዋል (2) ። በዚሁ መሠ

(1) Studi Etiopica-La lingua-et la storia di Harrar-cerulli ገጽ 34

(2) መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ገጽ 606

ረት ማር ጊዮርጊስ ፤ ማር ይስሐቅ ፤ ማር ኤፍሬም እንደሚባል ገላውዴዎስም ከመንግሥታቸው በፊትና ከነገሡም በኋላ ማር ገላውዴዎስ ይባሉ ነበር ማለት ነው (1) ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በሕይወታቸው ሳሉ የገላውዴዎስን ልዩ የመሪነት ችሎታ የተዋጊነት መንፈስ በመረዳት ከቀሩት ልጆቻቸው የበለጠ መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርት እየመገቡ እንደ አሳደጉዋቸው በቅድሚያ መንፈሳዊ መጻሕፍት ካስተማሩዋቸው በኋላ ቀጥሎ ፈረስ ግልቢያን አደንን በቀስት አመታትን የጦርነትን ትምህርት በነገሥታት ልጆች ሥርዓት እንደአስተማሩዋቸው ሲገልጽ ጠበንጃ አተኳኩስን ተማሩ አይልም (2) ። ይኸም የሚያስረዳን የሰለጠኑት አገሮች ለአደንም ለጦርነትም የሚጠቀሙበት ጠበንጃ በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ገብቶ አለመለመዱን ነው ።

ታሪከ ነገሥቱ ዓረብ ፋቂህ ጽሑፉን ከአቋረጠ ወዲህ ያፄ ልብነ ድንግልን የመጨረሻ ዘመን በተለይም ስለገላውዴዎስ ከቀድሞው ከአሜጭሩ ይልቅ በመጠኑ ሰፋ እያደረገ ይጽፋል ። ሰፋ አድርጎ የሚጽፈውም አብዛኛው መንፈሳዊ ንግግር ወይም ለአጻጻፉ ወዝ ለመስጠት ከራሱ አሳብ እያመነጨ የምስጋና ድርደራ ቢሆንም የደረቅ ታሪክ የጽሑፍ ቅርስ ላጣንበት ለዚህ ዘመን ይህን የታሪክ ነሥት ጽሑፍ መሠረታዊ ጽሑፍ አድርገን ሁልጊዜ እንጠቀምበታለን ።

በዚህ ምክንያት ታሪከ ነገሥቱ የዓፄ ገላውዴዎስን ልደትና ዕድገት ትምህርት ከዚሀ በላ[illegible]ንደተጻፈው ካመለከተ ወዲህ መልካሙን የስም ቅጽል ሁሉ ለርሳቸውና ለታሪካቸው እየከፋፈለ ይሰጣል ። የሚጽፈውን ታሪካቸውን "እንደማርና እንደ ስኳር ለአፍና ለጉሮሮ የሚጥም" እያለ ያመሰግነዋል (3) ። የበለጠ ደግሞ እራሳቸውን ከቡርና ልዑል ቡሩክና ቅዱስ እያደረገ ሥራቸው ካባቶቻቸው ይበልጥ የተመሰገነ ሥርዓታቸው ያማረ ሕጋቸው ንጹሕ ፤ ፍርዳቸው የቀና መሆኑን ዘርዝሮ ይናገርላቸዋል ። በዚህም ጸሐፊው ያሽከር ወዳጅ የነበረ ሊሆን ይችላል ወይም አነጋገሣቸውና አገዛዛቸው ያስደነቀው አሟሟታቸው ያሳዘነውና በፍቅራቸው የተነደፈ በኋላ የተነሣ ጸሐፊ ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ ሌሎቹም ጸሐፍተ ትእዛዛት ለየጌታቸው ሲጽፉ በዚሁ ዓይነት ነው ።

የሆነ ሆኖ ዓፄ ገላውዴዎስ ከአባታቸው ቀጥለው ሲነግሡ ይኸው የታሪካቸው መሠረት የሆነው ታሪከ ነገሥት ትክክለኛ ዕድሜያቸውን አይገልጽም ። ሕፃን (ወጣት) መሆናቸውን ብቻ እንደዚህ ሲል ጠቅሶታል «ሕፃን ሳለ ከልብነ ድንግል በኋላ ልጁ ገላውዴዎስ ስመ መንግሥቱ አጽናፍ ሰገድ ተብሎ ነገሠ» (4) ።

(1) የገላውዴዎስ ታሪክ ኮንዘልማን ያሳተመው ገጽ 13 - 17

(2) ወተምህረ ኵሎ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያናዊ ወእምድኅሬሁ ተምህረ ተፅዕኖ ፈረስ ወነዲፈ ቀስት ወንዒወ አራዊት ወኵሎ ሥርዓተ ፀብዕ ከመ ልማደ ደቂቀ ነገሥት ። ኰንዘልማን ያሳተመው ታሪካቸው ገጽ 8 - 9

(3) ዜና ሠናይ ለጥዑም ውስተ አፍ ወውስተ ጉርዔ እምጣዕመ መዓር ወሶከር ፡ ኰንዘልማን ያሳተመው የገላውዴዎስ ታሪክ ገጽ 1 - 2

(4) ወእምድኅሬሁ ነግሠ ወልዱ ገላውዴዎስ ወስመ መንግሥቱ አጽናፍ ሰገድ እንዘ ሕፃን ውእቱ ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 94

እንደ እውነቱ የሆነ እንደሆነ ታሪከ ነገሥቱን ያዘጋጀው ካህን ገላውዴዎስን ሕፃን በማለት ፈንታ ወሬዛ - ወጣት ሊላቸው ይገባ ነበር ። ሲነግሡ ትክክለኛ ዓመታቸው ባይታወቅም ብዙ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ከነዚሁም ውስጥ የፖርቱጋሉ ተወላጅ ቴሌዝና እንግሊዛዊው ብሩስ ፲፰ ዓመት አድርገውታል ፤ ሊመስል የሚችል ነው (1) ። ይኸም ሲሆን ግራኝ አህመድ በተነሣበት በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ላይ ዕድሜያቸው አራት ዓመት ስለሚሆን የመንፈሳዊም ሆነ የሥጋዊ ወይም የጦር ትምህርት ሲማሩ አደጉ ያለው በዚሁ በጦርነትና በመከራው ዘመን ነው ማለት ነው ።

ከአባታቸው ቀጥሎ ነገሡ ሲባልም በነጋሢነት መተካታቸውን ለማመልከት ካልሆነ በቀር በአሁኑ የግራኝ አህመድ የገዢነት ሥልጣን በመላ ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ በተለይ ንጉሣውያንን ቤተ ሰቦች በሚያሳድድበት ዓፄ ልብነ ድንግል ሞተው ሚስታቸውና ልጆቻቸው ግራኝና ጦሩ ሊወጣበት በማይችለው በደብረ ዳሞ ተራራ ሸሽተው በተቀመጡበት ሰዓት አባቶቻቸው በነገሡበት ወግና ሥርዓት ተደርጐላቸው እንደ ደንቡ በጳጳስ ተቀብተው እንዳልነገሡ የታወቀ ነው ። ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ከሞቱ ወዲህ በዚሁ በግራኝ ወረራ ምክንያት ከግብጽ ተተኪ ጳጳስ ግራኝ ከመሞቱ በፊት በፍጹም አልመጣም ።

ነገር ግን እዉኑው ፤ ዓታቤ ሰዓቱና ጽራግ ማሠሬው ከሞት የዳኑ እንዳሉ ወይም በሚቻቹ እግር ለስሙ እንኳን የተተኩት የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚያው ለአገርና ለወገን ታማኝነታቸውን ያላቋረጡት ባንድ የግራኝ ጦር በሌለበት ገለልተኛ ቦታ ሆነው የተለመደውን ሥርዓተ ንግሥ እንደተቻለ ፈጽመው ስመ መንግሥታቸውን አጽናፍ ሰገድ አሰኝተው ባባታቸው እግር እንግሠዋቸው ንግሣቸው በቅርብ ሆኖ ለሰማውና ለታመነው ታውጆ ይሆናል ።

ይኸም የነገሡበት ቦታና ቤተ ክርስቲያን ምንም ማስረጃ ከማጣት የተነሣ ማረጋገጡ ባይቻል በግምት ያው አባታቸው የተቀበሩበት እናቷቸውም ንግሥት ሰብለ ወንጌል እስከ ፖርቱጋሎቹ መምጣት ድረስ የኖሩበት የደብረ ዳሞ ተራራና የነገሡበት ገዳም የአቡነ አረጋዊ ገዳም ሳይሆን አይቀርም ።

## ምዕራፍ ፪

### ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡበት በመጀመሪያው ዓመት ከግራኝ አህመድ የጦር አለቆች ከወዚር አሳ ከገራድ ኡስማንና ከነድልበ ኢየሱስ ጋር ያደረጉት ጦርነት (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲፩ ቀን)

ታሪከ ነገሥቱ በዚህ ዓፄ ልብነ ድንግል በሞቱበትና ዓፄ ገላውዴዎስ በተተኩበት ዘመን አሸናፊነት ከአዳል ወይም ከሐረርጌ በመጡት እስላሞች እጅ መግባቱን በየጦርነቱ ግምባር ሁሉ ድል መንሣታቸውን አገሪቱን በአራቱም ማዕዘን ይዘው

(1) Historia I. II. CH. VII. ። ጀምስ ብሩስ የተወለዱበትን ዓመት እንደ አው. ቀ. ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. መሆኑን አመልክቶ ዕድሜያቸውን ፲፰ ዓመት አድርጎታል ። J. Bruce Tome II. ገጽ 187 ።

በጥሩ ጥሩ ከሕንድ አገር በመጣ ደንጊያ በብርና በወርቅ እየተጌጡ የተሠሩትን አ[illegible] ያት ክርስቲያናት አቃጥለው ማፈራረሳቸውን ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በሰይ[illegible] መገደላቸውን የቀሩትም ወጣቶች ሕፃናት ሴቶቹም ወንዶቹም ለግብር መሸ[illegible] ውን በዚህም ጊዜ ብዙዎች የክርስትና ሃይማኖታቸውን እየተዉ መስለማቸው[illegible] ሃይማኖታቸውን ሳይለውጡ የጸኑት ከአሥር አንድ አለመሆናቸውን ያረጋግጣል

እንደዚሁም በዚሁ ዘመን ባገር ላይ ረሃብ ወርዶ ስለነበረ ዓፄ ልብነ ድንግል ከወረዳ ወደ ወረዳ ከበረሃ ወደ በረሃ በረሃብና በጥማት እየዞሩ ከልጆቻቸውና ከቤተ[illegible] ሰቦቻቸው ግማሾቹ በሰይፍ ሲያልቁ የቀሩትም በምርኮ ሲወሰዱ ንጉሡ ልብነ ድን[illegible] ግልና ገላውዴዎስ በእግዚአብሔር ተጠብቀው ባንድነት ሆነው በደረሰባቸው መከራ በእግዚአብሔር ላይ ምንም ጽርፈት (ማንጎራጎር ወይም የብስጭት ንግግር) ሳያሰሙ በትዕግሥት አሳልፈው በመጨረሻ ልብነ ድንግል ከዚህ ዓለም ድካም ሲያርፉ እግዚአብሔር የዕውቀት የጥበብ የትዕግሥት የማስተዋል ዕድልና በረ[illegible] ጨምሮ ልጃቸውን እንዳነገሣቸው ፤ ከነገሡም በኋላ ወደ ቡርክሉሜዳ መሄዳቸ ውን ይገልጻል (1) ። ወደ ቡርክሉሜዳ የሄዱት ከወደቁት ተነሥተው መሆኑን እያ ነሣም ምናልባት አባታቸው ከሞቱበት ከደብረ ዳሞ ሊሆን ይችላል ።

የሆን ሆኖ ታሪከ ነገሥቱ በዚሁ በቡርክሉሜዳ ስለአደረጉት ጦርነት የሚለ ውን ቃል [illegible] ግዕዙ ወደ አማርኛ ሲተረጐም የሚሰጠውን ቃል እንመልከት «ከዓፄ ልብነ ድንግል በኋላ ሕፃን ሳሉ ስመ መንግሥታቸው አጽናፍ ሰገድ ተብ ለው ገላውዴዎስ ነገሡ ። ከዚያ ተነሥተው ቡርክሉሜዳ ደርሰው ከወዚር አሣ ከገ ራድ ኡስማን ከድልበ ኢየሱስ ከኢዮአራምና ከሌሎቹም እስላሞች ጋር በድንገት ተገናኝተው በታኅሣሥ ፲፩ ቀን ተዋግተው ብዙዎችን ገደሉ ። እንደሚያስፈራ አን በሳ ፤ አራስ ቤት እንዳለች (እንደወለደች) ድብ ገርምመው አስደነገጧቸው ። ከለ ዲዎቹም እፊታቸው መቆም አቅቷቸው እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ስለሆነ ማ ሊዋጋ ይችላል ተባባሉ ። ይኸንንም የሠሩት እሳያቸው ባለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው ። ከዚች ቀን በቀር የጦርነትን ደንብ ተምረው በጦርነትም ላይ ውለው አያውቁም» (2) ።

ይኸን ታሪከ ነገሥት ያዘጋጀው የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ሰው ለአነ ጋገሩ ወዝ ለመስጠት በተለይም በታሪክ አጻጻፉ በነጋሚው ወይም በልጁ ፊት ተመስግኖ ጽሑፉ እንዲወደድለት ሲል ብዙ ቃለ አጋኖ ከእውነተኛው ታሪክ ጋር

(1) . . . . . .ወበዘከመዝ ግብር ዝንቱ ወልድ ወአቡሁ ነበሩ እመራተ ዓመታተ እንዘ ይትቄከ ዙሉ በእኩቴት ዘይመጽእ ላዕሌሆሙ ወእንዘ ኢይሁቡ እበደ ላዕለ እግዚአብሔር አምላኮሙ ንጉሠ ኢዶም . . . . . . ኮንዘልማን ያሳተመው የገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ምዕ. ፩ ገጽ ፪

(2) ወእምድኅረዝ ነግሠ ወልዱ ገላውዴዎስ . . . . . እንዘ ሕፃን ውእቱ . . . . . . ወተራከበ ምስለ ወዚር ዓሳ ወገራድ ኡስማን ወድልበ ኢየሱስ ወኢዮራም . . . . . . ወገብረ ፀብአ ምስሌሆሙ አመ ፲ወ፩ ለታኅሣሥ ፤ ወቀተለ ብዙኀነ ወገረሞሙ ከመ አንበሳ መፍርህ ወከመ ድብ ሐራስ ፤ ሐሩ ወኢክህሉ ቀዊመ ቅድመ ገጹ ፤ ወይቤሉ መኑ ይክል ፀቢአቶ እስመ እግዚአብሔር ምስሌሁ . . . . . . ታሪከ ነገሥት ገጽ 94 ።

እሚፍር እንደጨመረ ይታያል ። እውነተኛውን የሆነውንና ሳይሆን ለቃለ አጋኖ የተጨመረውን የመለየቱ ጉዳይ በአሁኑ ዘመን የጸሐፊውና የአንባቢ ጉዳይ ነው ። በዚህም ላይ በፊተኛው ምዕራፍ ላይ "አደንን ቀስት አወራወርን የጦር ትምህር ትን ተማሩ" ካለ በኋላ ባሁኑ ምዕራፍ ደግሞ "ከዚች ቀን በቀር የጦርነትን ደንብ" እንዳልተማሩ ስለሚገልጽ ጸሐፊው ሁለቱን ጉዳይ አላገናዘበውም ።

እውነቱ ዓፄ ገላውዴዎስ ጦር ይዘው ከነገራድ ኡስማን ጋር መዋጋታቸው ከእስላሞች ውስጥም ሊገድሉ መቻላቸው ነው ። ነገር ግን በዚህ በነገሡበት ዓመት በታኅሣሥ ፲፭ ቀን በተደረገው ጦርነት እንኳን እንደ አንበሳ ገርምመው ሊያሳድዱ ማሸነፋቸው እንኳን ያጠራጥራል ። ምክንያቱም ከዚህ ጦርነት በኋላ ታሪከ ነገሥቱ ራሱ በሌላ ቦታ ላይ ወደ ተራራማው አገር ወደ ስሜን መሄዳቸውን ስለሚገልጽ በትንሽ ጦርና በድፍረት በቡርከሎሜዳ ተዋግተው ምንም አንዳንድ ወይም ብዙ እስላሞች ቢገድሉ መሣሪያና ጊዜ ያደላላቸው የእስላሞቹ ሹማምንት እነወዚር ዓሣ ከአገር ተወላጆቹ ሹማምንት ከነድልበ ኢየሱስ ጋር ሆነው መልሰው በመውጋት ስለበረቱባቸው የእናታቸው ወገን ወደ ሆነው ተራራማ የስሜን አገር ሄደው በመቀመጥና በዚያ ለሌላው ጦርነት እንደገና ለመደራጀት አስበው ይሆ ናል ።

በዚህ ምክንያት "እንደ አንበሳ ገርምሞ አስደነበራቸው" ወይም "በዚህ ፊት ማን ሊቆም ይችላል ተባባሉ" የሚ[illegible]ትክክል ለቃለ አጋኖ ጸሐፊው ካሀን የጨመረው እንጂ በአሁኑ ሰዓት ይኸን የመሳሰለው የፍርሃት ስሜትና አነጋገር ከእስላሞቹ በኩል ሊሰማም ሊነገርም እንደማይችል ግልጽ ነው ።

መቼም ግራኝ አህመድ ከነጦሩ ሊጠቃ የሚችልበት ሁለት መንገድ ብቻ ነው ።

፩ኛ. እንደርሱው ወጣት በሆነ ሞትን በማይፈራ ርሱ ራሱ ባፄ ልብነ ድንግል ላይ እንዳደረገው የጦርነቱን አመራር ራሱ እየተቆጣጠረ በድፍረት በሚዋጋና በሚያዋጋ መሪ ፤

፪ኛ. ቢቻል ከርሱ የበለጠ ያለዚያም እርሱ በያዘው መጠንና ዓይነት የጦር መሣ ሪያ በያዘ ጦር ሠራዊት ነው ።

እነዚህ ሁለቱ ሳይነጣጠሉ ባንድነት ሲገኙና ሁለቱ ባላጋራዎች ሲዋጉ እዚህ ላይ የጦርነቱን ዕድል የሚወስነው ይበልጥ ጀግንነትና መስዋዕትነት ያሳየው ወገን መሆኑ የታወቀ ነው ።

ቀድሞ ጦርነቱ ሲጀመር በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ግራኝ የ፳፩ ዓመታት ወጣት ሲሆን ዓፄ ልብነ ድንግል የ፴ ዓመት ጐልማሳ ነበሩ ። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የየመሪ ዎቹ ዕድሜ ተዘዋውሮ ዓፄ ገላውዴዎስ የ፲፰ ዓመት ወጣት ሲሆኑ ግራኝ አህመድ ፴፫ ዓመት ሆኖታል ። ቢሆንም ይህ የወጣትነት ዕድሜና የድፍረት ውጊያ ብቻ ያለ መሣሪያ ሊያገለግል አይችልም ። ግራኝ አህመድ በወጣትነቱ በድፍረቱ በመ ሪነት ችሎታው ላይ ከባሕር ማዶ የመጡለት አዳዲስ መድፎች ከሰለጠኑ ተዋጊ ዎች ጋር ባይጨመሩለት ኖሮ ምንም እንኳን ከወደ መጀመሪያው ዘመን ላይ በድ

ፍረት እየተዋጋ ቢያሸንፍ ያለዚህ መሣሪያ እስከ መጨረሻ ሞታቸው ድረስ ዓፄ ልብነ ድንግልን ለመጣል ባልቻለ ። አሁንም ጊዜውና ነገሩ ተዘዋውሮ ዓፄ ገላውዴዎስ ምንም ወጣት ደፋር ተዋጊ እንደ ጸሐፊው አባባል የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸው ቢሆኑም እንደ አንበሳ ቢያስፈሩም ከፖርቱጋል መንግሥት ለእርዳታ የተላኩትን ወታደሮች ከነመሣሪያቸው ከማግኘታቸው በፊት የደረጀውን የግራኝ አህመድን ጦር ሊበግሩት አይችሉም ። የዚህንም ሁኔታ ወደፊት በየምዕራፉ በዝር ዝር እናነባለን ።

ነገር ግን በማናቸውም ረገድ የዓፄ ልብነ ድንግል በግራኝ እጅ ሳይወድቁ መሞት ፤ አሁን የወጣቱ የዓፄ ገላውዴዎስ መንገሥና ጦር መሰብሰብ ፤ ፊት ለፊት ከግራኝ ጦር ጋር በድፍረት መግጠማቸው ፤ ለግራኝ ሳይገብሩ በየጫካው በየበረሃው በሚገኙት አርበኞች ፊት ፤ በፍርሃት የተነሣ ለሕይወታቸው እየሳሱ መሸፈት ያልሆነላቸው ከመሞት መሰንበት በሚባለው ፍልስፍና ተጠምደው ያለልባቸው ሃይማኖታቸውን በግዴታ እየለወጡ ለእስላሞቹ እየገበሩ በተቀመጡት ዘንድ የተስፋ ጮራ እያሳዩ የደኅንነት ተስፋን እንደሚያሳድሩ አይጠረጠርም ።

ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡበት ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋጉበትን የዚህን የጦርነት ቦታ ታሪከ ነገሥቱ ቡርከሎሜዳ እንዳለው ተመልክተናል ። አንዳንዱ መጽሐፍ ይኸንኑ ቦታ ቡርከሎ መከዳ ወይም ጉሎ መከዳ እያለ ያጭበረብረዋል (1) ። ሥፍራው በትክክል ቡር ሳይሆን አይቀርም ። ቡር የሚገኘው በትግሬ ግዛት በተለይ በሠራዬና በደባርዋ መካከል መሆን አለበት ። ጉሎ መከዳ ግን በዛሬው የአገዛዝ ድልድል በአጋሜ የአውራጃ ግዛት ውስጥ የወረዳ ግዛት ሆና ከተማው ዛላ አንበሳ ይባላል (2) ። ጉሎ መከዳን ባላገር ጉልቷ ለማከዳ እያለ በመኖራት ፍቺ መስጠቱን ሰምቻለሁ ።

ባዔ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት (፲፭፻፺፱ - ፲፮፻፳፬ ዓ. ም.) ስሜ ያዕቆብ ነው ያዔ ሠርፀ ድንግል ልጅ ነኝ ብሎ ለመንገሥ በሸፈተ ጊዜ በባሕረ ኤርትራ አጠገብ ያሉ ወረዳዎች ሽፍታውን ደግፈዋል ተብሎ ስለተወራ ንጉሡ ዓፄ ሱስንዮስ የዘመቱባቸውን ወረዳዎች ዜና መዋዕላቸው ሲቆጥር ሰብእ ተደረር ወቡር ወሺሖ ወደር ቤታ እስመ እሙንቱ ኮኑ በወሰነ ባሕረ ኤርትራ ይልና ከዚያ አልፍ ብሎ ደግሞ ረሰየ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከተማሁ በምድረ ቡር . . . . . ወተመይጠ ንጉሥ እምድረ ቡር ሖረ መንገለ ደባርዋ ይላል (3) ።

ስለዚህ ዓፄ ልብነ ድንግል ሠራዬ ሞተው በደብረ ዳሞ በተቀበሩበት ጊዜ ወጣቱ ገላውዴዎስ ምናልባት ከዚያው ግራኝ ሊደርስበት ከማይችለው ከደብረ ዳሞ ተራራ ላይ በሚገኘው በአቡነ አረጋዊ ገዳም ሥርዓተ ንግሣቸውን እንዳከበሩ ከዚያ ወርደው በዚሁ በሠራዬ ውስጥ በሚገኘው በቡር ከነገራድ ኡስማን ጋር

(1) Etudes sur l'histoire d'Ethiopie - René - Basset ገጽ 18. 109 - 110 ። ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ማስታወሻ ገጽ 94 ፤

(2) ያገር ግዛት ሚኒስቴር ያወጣው ዝርዝር . . . . . . . ገጽ 16

(3) Chronica de Susenyos ምዕ . 38 ቊጥር 112

ከተዋጉ በኋላ ሳይሸነፉም ሳያሸንፉም ወደ ሰሜን በግሥጋሤ ሄደዋል ማለት ነው ።

ፓሪስ ፩፻፵፫ ቍጥር ተሰጥቶት የተቀመጠው ታሪከ ነገሥት በዚህ ዓይነት የመዠመሪያውን ዓመት የንግሣቸውን ጦርነት ሲተርክ ሌላው ከአከስፎርድ (እንግሊዝ አገር) አግኝቶ ውሊያም ኮንዘልማን ያሳተመው ገላውዴዎስ ወዲያው እንደ ነገሡ ከወዚር አባስ ጋር መዋጋታቸውን ፤ ከዚያ ከትግሬ ፪ ወንዞች ተሻግረው ወደ ሸዋ ሄደው በደዋሮ ከግራኝ ልጅ ከነስረዲን ጋር መዋጋታቸውንና በኋላ ደግሞ ከሸዋ ወደ ትግሬ መመለሳቸውን ይተርካል (1) ።

## ምዕራፍ ፲፬

## ዐፄ ገላውዴዎስ በሰሜን ከገራድ ኡስማን ከወዚር ሙጃሂድና ከናስር አዲን ጋር እንደተዋጉ (በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. የካቲት - ሚያዝያ)

ዓፄ ገላውዴዎስ ባለፈው ምዕራፍ ያነበብነውን ጦርነት ቡር ከሎሜዳ ላይ ካደረጉ በኋላ ወደ ሰሜን ሄደዋል ። በቡርከሎ ሜዳ ከተዋጉ በኋላ ወደ ሰሜን ያመሩበት ምክንያት ከዚህ በፊት እንዳልነው ፩ኛው በሰሜን በእናታቸው በኩል ሰለሚወ ለዱ አገሬው እንደሚቀበላቸው በመረዳት ፪ኛው ደግሞ ከዚህ በፊት በንአዝማች ሻውል ጦርነት ዘመን እንደተመለከትነው አገሩ ተራራማ ከመሆኑ የተነሣ ትንሽ ጦር ይዞ ብዙ ቀን ጠላትን ለመከላከል መቻሉን ተመልክተው መሆን አለበት ። በእርግጥም ወደ ሰሜን በሄዱ ጊዜ በሰሜን ያሉ የአገውና የጸለምት ሰዎች . . . . . . ተቀበሉዋቸው (2) ።

ነገር ግን የዓፄ ገላውዴዎስ ወደ ሰሜን መሄድ እንደተሰማ የግራኝ ዋና ዋና የጦር አለቆች ወዚር ሙጃሂድ ፤ ገራድ ኡስማን ገራድ ናስር አዲን በሺሬና በሥራዬ የሚገኘውን ጦራቸውን ይዘው ተከታትለው ሄደው ወግተዋቸዋል ።

ወዚር ሙጃሂድ ከሥር ዠምሮ በየጊዜው በክርስቲያኖቹ ላይ የፈጸመው ሁሉ በየምዕራፉ ስለተጻፈ ከዚህ ላይ ደግሞ ማስታወስ አስፈላጊ አይደለም ። ገራድ ኡስማንም ከብዙ ሥራው ጋር ከሁለት ዓመት በፊት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. የንጉሡን የበህር ልጅ ፊቅጦርን የገደለ ነው ። ገራድ ናስር አዲንም (ግዕዙ ነስረዲን የሚለው) የባሌ ገራድ ልጅ በብዙ ቦታ ሲዋጋ የኖረ ነው ። ከነዚህ ከሦስቱ ገራድ ኡስማን ባለፈው የታኅሣሥ ወር ገላውዴዎስን ተዋግቷል ። እነዚህ የግራኝ ሹማምንት ተሰብስበው ከሄዱበት በኋላ ገላውዴዎስ በመካከላቸው ፫ ወር ሲኖር የተዋቤኑን ሹም የሄኖክን ልጅ ከሐዲውን ዮናታንን ገድሎ ለመንግሥት የሚገባውን ግጸ በረከትና ግብር ሲቀበል ሊዋጉት አልቻሉም ከማለት በቀር ያልተዋጉበትን ምክንያት ምንም ታሪከ ነገሥቱ ባይዘረዝረው ባዔ ገላውዴዎስ በኩል በዚህ ጊዜ የሚደረገው

Chronique de Gelawdewos chap. VIII-X.

(2) ታሪከ ነገሥት ገጽ 94

የደፈጣ ጦርነት ኖሯል ማለት ነው ። ከሐዲውንም ዮናታንንም በድንገት አርበኞች ደርሰው ገድለውት ይሆናል ።

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ባሁኑ ጊዜ ዓፄ ገላውዴዎስ ያላቸው ጦር መጠነኛ ከመሆኑ የተነሣ በትንሽ ጦር የበረከተውን የእስላሞች ጦር በመውጋትና ጦራቸውን በመጉዳት ፈንታ የስሜንን አገር ተገን አድርገው ሲመቻቸው ከስሜን ወደ ተምቤን በዚህ በወጣትነታቸው ጊዜ በግሥጋሤ እየሄዱ አደጋ በመጣል በመንገዳቸው የአጋጠማቸው ሕዝብም እየተደሰተ ገጸ በረከትም ግብርም ተቀብለው ሳይመቻቸው ደግሞ ለፈረስና ለበረከተ ጦር የሚመቸውን ሜዳማ ሥፍራ እየለቀቁ ወደ ስሜን ይመላለሱ ነበር ማለት ነው ።

በዚህ ምክንያት በፊተኛው ከቡርክሎ ሜዳ ጦርነት በኋላ ወደ ስሜን መሄዳቸውን እንደገለጸልን አሁንም በተምቤን ዮናታንን ገድለው ካገሩ ላይ ለመንግሥት የተገባውን ገጸ በረከትና ግብር ተቀበሉ ካለ በኋላ በተምቤን ሳይቆዩ ተከዜን ተሻግረው ወደ ምድረ ሰርድ ሄደው የትንሣኤን በዓል አከበሩ ስለሚል ምንም እንኳን ምድረ ሰርድ ያለበትን ትክክለኛ ሥፍራ ባላውቀው ከተምቤን ሄዶ የተከዜን ወንዝ ለተሻገረ ሰው የሚገኘው ያው የጸለምት ወረዳ ስለሆነ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚሁ ተራራማ ወይም በረሃማ ሥፍራ ተመልሰው የፋሲካን በዓል አክብረው ሳለ እንደገና ገራድ ኡመር በሚያዝያ ፳፱ ቀን ከተዋጋቸው በኋላ ሁለተኛ ጊዜ ወደ ስሜን መመለሳቸውን ያስረዳል (1) ።

ታሪከ ነገሥቱን ያዘጋጀው ካህን አንዳንድ ጊዜ ከእውነት ላለመውጣት ሲበነቀቅ ጦርነት መደረጉን ሲጠቅስ ተዋግተው አሸነፉ አይልም ፤ ተሸንፈው ወደ ስሜን ሸሹ ማለትንም አይፈልግም ። ነገር ግን የዘመኑ የአጻጻፍ ልማድና የወገንነት ባሕርዩ እያስገደደው ወይም የወጣቱን ንጉሥ ዝና የማሳመር ፍላጐት ሲመጣበት እስላሞቹ በዚህ ጊዜ ለመናገር የማይችሉትን እነጋገር በመጨመር "በትንሽ ሠራዊት እየተዋጋ ሕፃን ሳለ ሞትን የማይፈራ እንደዚህ ያለ ጐበዝ ዠግና ዓይተንም ሰምተንም አናውቅም" አሉ በማለት ከዠመረው የጥንቃቄ አጻጻፍ ይወጣል (2) ።

ይህ ዓይነት አጻጻፍ ከዚህ በፊት እንደ አንበሳ ገርምሞ አስደነበራቸው ካለው ጋር ተደባልቆ ለዚያን ዘመን አጻጻፍ ተገቢ የመሰለ የተለምዶ የቃል አደራደር መሆኑን ተገንዝበን በዛሬው አስተሳሰባችን ሐቁን ታሪክ ለአድናቆት ከተጨመረው ንግግር እየለየን መገንዘብ እንችላለን ።

በዚህም ላይ ወጣቱ ንጉሥ ብዙ ጦር እንደሌላቸው በእርግጥ የታወቀ ስለሆነ ሁለት ጊዜ ወደ ስሜን መሸሻቸው የታወቀ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ከስሜን እየመጡ አደጋ ለማድረግ በመድፈራቸው "እንደዚህ ያለ ጐበዝ ዠግና ዓይተንም

(1) ታሪከ ነገሥት ገጽ 94

(2) ወእንዘ ሀሎ ሕየ መጽአ ኃቤሁ ገራድ እመር (ኡመር) ወተመጠውዎ በሰላፍ ወገብሩ ፀብዓ አመ ፳ወ፱ ለሚያዝያ ወይቤሉ ኢርኢነ ወኢሰማእነ ዘከመዝ ኃያለ ወተባዓ እንዘ ሕፃን ውእቱ ዘኢይፈርኅ ሞተ አኮ በብዙኃ አላ በውሑድ ወእምዝ ሖረ ምድረ ስሜን . . . . . ታሪከ ነገሥት ገጽ 94

ሰምተንም አናውቅም'' ባይሉ እንኳን እንዴት ይኸ ወጣት ደፍሮ በመካከላችን ገብቶ ይኸን ሥራ ብለው ወደ መገረም ሳይደርሱ አይቀርም ብሎ ለማመን ይቻላል ። ከመገረሙም ጋር መደምደሚያውን ገላውዴዎስ ወደ ሰሜን እየሄዱ ስለማይጠመዱ በእስላሞቹ ዘንድ ምናልባት ጸጸትም ንቀትም ይኖርበት ይሆናል ።

ባፄ ገላውዴዎስ እንግሥ ካለመሥጋት የተነሣ ጦርጦራ ተዋጊ ዓፄ ልብነ ድንግልን ያለ ዕረፍት አባራሪ የነበረው ግራኝ አህመድ በአሁኑ ሰዓት ያገሩ ጌታ የሆነው በደምቢያና በሌሎቹም አውራጃ እየተዘዋወረ ተድላ ደስታውን ከመፈጸም በቀር ፖርቱጊዞች ከመምጣታቸው በፊት አንድ ጊዜም ጦር ይዞ በዓፄ ገላውዴዎስ ላይ ራሱ አልዘመተም ። ይኸን በመሰለው ዓይነት ጠላትን ከመዠመሪያው ላይ በመናቅ ስሕተት ዓፄ ልብነ ድንግል እንደወደቁ እርሱም ወድቆበታል ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ በግራኝ አህመድ አነሣሥ ዋዜማ የኢትዮጵያ ሁኔታ ምን ዓይነት እንደነበረ ባጭሩ በዚህ መጽሐፍ በመዠመሪያው ክፍል እንደተመለከትን አሁን ደግሞ ዓፄ ልብነ ድንግልን ጋብቻ ጠይቆ የእምቢታ መልስ ካገኘ ወዲህ ግራኝ አህመድ በንዴት ዓፄ ልብነ ድንግልን በጦር እያዋከበ ከቤተ ሰቦቻቸው ግማሹን እያስገደለ ግማሹን እያስማረከ የጦርነትና የስደቱን መከራ በክርስቲያኑ ንጉሥና ሕዝባቸው ዘንድ ባጸናበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን ከመሰለው መከራና ስደት በሞት ከተገላገሉ በኋላ ልጃቸው ገላውዴዎስ ፲፭፻፵፩ን ተከትለው ባለፉት ምዕራፎች ያደረጉትን ውጊያዎች በፈጸሙበት ወቅት የቱርክና የፖርቱጋል የመርከበኛ ጦር በዓረብና በሕንድ አገር ወደቦች ላይ ውጊያቸውን አላቋረጡም ።

የግራኝ ውድቀት የኢትዮጵያ ትንሣኤ የተገኘው ከሁለቱ ጦርነት መካከል ነው ። በመዠመሪያ የቱርክ የመርከብ ጦር በሶሊማን ፓሻ እየተመራ ከስዌዝ ተነሥቶ የቀይ ባሕርን አልፎ በሕንድ ያለውን የዲውን ወደብ ደብድቦ ከተመለሰ ወዲህ የዚህን ብድር ለመመለስ በሕንድ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ እስጢፋኖስ ደጋማ ከጐአ ወደ ስዌዝ ዘምቶ ከስዌዝ በተመለሰበት ሰዓት ከዓፄ ልብነ ድንግል እርዳታ ሊጠይቅ ወደ ሊስቦን የሄደውን ቤርሙዴዝንና በታናሽ ወንድሙ አዝማችነት ፬፻ የፖርቱጋል ወታደሮችን ምጥዋ ላይ አራግፎ ኢትዮጵያን እንዲረዱ አደረገ ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ግራኝን ለመጣልና መንግሥታቸውን ለማቆም የቻሉት በነዚህ እርዳታ ስለሆነ አሁን በኢትዮጵያ የትንሣኤ ዋዜማ ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በየወደቡ ያደረጉትን ጦርነት በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመልከት ። ይኸንንም መመልከት ፖርቱጋሎቹ ከመጡ በኋላ የተደረገውን ጦርነት በሰፊውና በግልጽ ለመረዳት ይጠቅማል ።

## ምዕራፍ ፲፰

## የሶሊማን ፓሻ ጉዞ ወደ ዲው ወደብ (ሕንድ)

ግራኝ አህመድ የትግሬን ፣ የቤገምድርን የጐጃምን ወረራ በሚያከናውንበት ጊዜ በአውሮፓ የፈረንሳዊ ንጉሥ ፩ኛ ፍራንሷና ሻርል ፭ኛ በሚዋጉበት ሰዓት ፣ በአፍሪካ ምሥራቅና በዓረብያ ምዕራብ በሚገኘው ግራና ቀኝ የቀይ ባሕር ወደቦች ላይ እንደዚሁም በፖርቱጋል ቍጥጥር ውስጥ ባሉት በሕንድ ወደቦች ላይ የግራኝ ደጋፊ የሆኑት ቱርኮችና እኛን ለመደገፍ ተሰፋ ተጥሎባቸው የነበሩት ፖርቱጋሎች በየጊዜው ከመዋጋት አላቋረጡም ። ውጊያው የግዛት መስፋፋት የቅመማቅመምና የሸቀጣ ሸቀጥ የንግድ ጥቅም አለበት ። ኃይል ያገኘው ወገን ነዋሪ ባላባቶቹን አሸንፎ ካስገበረ በኋላ ወደቦቹን ይዞ መቈጣጠር የቻለው ለመዋጊያ መልካም ምሽግ ከማግኘቱ በቀር በወደቡ አማካይነት ከዓረብና ከሕንድ አገር የሚገኘውን ተፈላጊ ሸቀጣሸቀጥ ላውሮፓ የአውሮፓን ዕቃ ለነዚህ አገር ሕዝቦች በመሸጥ ያንዱ አገር ዕቃ ለሌላው ብርቅና ተፈላጊ ስለሆነ በዚህ ንግድ የሚገኘው ጥቅም ከፍ ያለ ነው ። በዚህም ሰበብ የየግልን ሃይማኖት ለማስፋፋት የሃይማኖት ወገንን ለመርዳትና ለመደገፍ ያመቻል ።

በዚህ ጊዜ በንግድ ስመ ጥር የሆነችው ቬኒሲያ ከቱርክና ከፖርቱጋል በጦር ኃይል በመፎካከር ሳይሆን ከአሸናፊው ጋር በመስማማት በመርከብ ጉዞና በንግድ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዛ የኖረችበት ጊዜ ነው ። አንዳንድ ጊዜም ኃይል ሲሰማት ከቱርክ መርከበኞች ጋር የተዋጋችበት ጊዜ አለ ። አንዳንድ ጊዜ በዕውቀት የቬኒሲያ ተወላጅ ቢበልጥም በኃይልና በወታደር ብዛት ቱርክ እየበረታ ቱርኮቹና ቬኒሲያዎቹ በሚዋጉበት ጊዜ የቬኒሲያዎቹ ተወላጆች ከውጊያ ላይ ተሸንፈው እየተማረኩ ከምርኮ በኋላም አሽከርነት እየተቀጠሩ ለማራኪያቸው ለቱርክ ዕውቀታቸውንና አገልግሎታቸውን ያበረክታሉ (1) ።

የሆነ ሆኖ እንደ ሰላጤ የገባው የቬኒሲያ ሬፑብሊክ ኃይል በመዳከም ከትግሉ ከመውጣቱ በፊትና በኋላ በባሕርም በየብስም ኃይላቸው ባሁኑ ጊዜ ተመዛዛኝ የሚዋጉት ፖርቱጋሎችና ቱርኮች ናቸው ። በፊተኛው ዘመን (፲፭፻፰ - ፲፭፻፲፫) የግብጽ ግመሉኮች በቱርክ በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ከመደምሰሳቸው በፊት የፖርቱጋል ባላጋራ ሆነው በሱልጣን ኤል ጉሪ ዘመን ሚር ሁሴን የሚባለው በአደን ወደብ ላይ ከፖርቱጋሎቹ ጋር ተዋግቶ ከዚያም ዲው እስከሚባለው የሕንድ ሰሜናዊ ወደብ ዘልቆ በሎሬንሶ ዳልሜይዳ ከሚመሩት መርከበኞች ጋር (፲፭፻፰ - ፲፭፻፱ ዓ. ም.) ተዋግቶ ለማሸነፍ ጥቂት ሲቀረው እንደገና ተሸንፎ በሽሽት ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ነገር ግን ግብፅ እ. አው. ቍ. በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. በቱርክ ጦር ተሸንፋ እንዳካባቢው አገር ሁሉ በቱርክ ሱልጣን ሥር ከተጠቀለለች ወዲህ በተለይ በአሁኑ ጊዜ

(1) La mer rouge l'Abissinie et l'Arabie A. Kammerer ገጽ 71 - 72

እንደ እው. ቀ. ከ፲፭፻፴፯ ዠምሮ እስከ ፲፭፻፵፩ ዓ. ም. ድረስ በየወደቡ የሚደረገው ጦርነት በቱርክና በፖርቱጋል መካከል ሆነ ። ይሁን እንጂ ቱርክ የበላይ ባለ ሥልጣንና ሩቅ በመሆኑ ባፄ ልብነ ድንግል ላይ የጦር መሣሪያ እያስታጠቁ ወታደር እየመለመሉ በመላክ ያስቸገሩት የዓረብ አገር የጅዳ የየመን የአደን የሞካ የሐድራሞት መሳፍንት ሁሉ በመዠመሪያው ጊዜ ላይ በነፃነት በራሳቸው ሲተዳደሩ አንዳንድ ጊዜም ፖርቱጋል ማየሉን ሲያዩ ለፖርቱጋል ንጉሥ እንገብራለን እያሉ ቆይተው ሳለ አንድ ባንድ በቱርክ ጦር እየተመቱ በመጨረሻው የቱርክ ተገዥነታቸውን እምነው ለቱርክ ግዛት መስፋፊያ ዋና መሣሪያ ሆነዋል ።

እነዚህም ባላባቶች በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካከል የተወጠነውን ዝምድና ስለሚያውቁ ባንድ ወገን ለግራኝ አህመድ ጦር እየላኩ ዓፄ ልብነ ድንግልን ሲያስወጉ በሌላው ወገን ደግሞ ለኢትዮጵያ ረዳት ከመሆን ጋር አደንን ምጥዋን ዘይላን እልፍ እልፍ እየወጋ ያስቸገራቸውን የፖርቱጋልን ጦር እንዲወጋ በመላክ በሃይማኖት የሚቀርባቸውን ቱርክን ያሳስቡ ነበር ።

ቱርክ ይኸን ሁሉ የዓረቦች ወደብ ከመግዛቱ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ አህመድ (ነጂው) የእስክንድር መዝ ልጅ ግራኝን እንደልቡ እንዳይረዳ በሲልቬይራ የሚመራው የፖርቱጋል ጦር አደንን ከያዘና የአደኑ መስፍን የፖርቱጋል ንጉሥ ገባርነቱን አምኖ ባመት ፲፫ የወርቅ ፓርዶስ (?) ሊገብር ግዴታ ስለገባ ከዚያም አልፈው ፖርቱጋሎች በሐ[illegible]ት በሶኮትራ በማህራ ስለገቡ ቀጥሎም በሕንድ በጐአ እንደዚሁም በዲው ግዛታቸውን ስላጸኑ ሁኔታው በማናቸውም ረገድ የቱርክን ሥልጣን የየወደቦቹን ባላባቶች የሃይማኖትና የንግድ ጥቅም ስለተቃወመ በማናቸውም ረገድ የቱርክ መንግሥት በሶሊይማን ፓሻ የሚመራ የጦር መርከብ አዘጋጅቶ የዚህን ክፍል ግዛት በራሱ ቁጥጥር ውስጥ ለማድረግ ከፍ ያለ የጦር መርከብ ዝግጅት አደረገ ።

በመዠመሪያ የቱርክ የጦር መርከብ ሊወጋ የተዘጋጀውም እ.እው.ቀ. ከ፲፭፻ ፴፰ ዓ. ም. ዠምሮ ፖርቱጋሎች ይዘው የጦር መርከባቸውን ያደረጁበትን በሕንድ ሰሜን ከጉዜራት ወደ ደቡብ የምትገኘውን የዲውን ወደብ ሆኖ በዚያ የሚገኘውን የፖርቱጋልን የጦር ኃይል ለመደምሰስና የሕንድን እስላሞች ወደራሱ ግዛት ለመደረብ ነው ። ወደቧ በጋምባያ መስፍን ግዛት ውስጥ ስለሆነች መስፍኑም እስላም ከመሆኑ የተነሣ እርሱና በሕንድ ያሉት የእስላም መሳፍንት ላዩን ኃይሉን መቃወም እያቃታቸው ለፖርቱጋል እየገበሩ ውስጡን ደግሞ ከክርስቲያኑ ከፖርቱጋል አገዛዝ አድነን እያሉ በስጣንቡል ለሚቀመጠው ለዋናው የቱርክ ሡልጣን ለሶሊማን ይልኩ ነበር ።

በዚህ ምክንያት በቱርክ ሡልጣን ፈቃድና ትእዛዝ ወዚር ሶሊማን እል ካዲም (ባጭሩ ሶሊማን ፓሻ) የሚባለው በስዌዝ (ግብፅ) ወደብ ላይ የጦር መርከቦቹን በደንብ አዘጋጅቶ የፖርቱጋልን ኃይል ለመደምሰስ ተነሣ ። ሶሊማን ፓሻ ዘሩ ግሪክ ቁመቱ አጭር ወፍራም ቶንጋ ግፈኛ ጨካኝ ከዳተኛ መሆኑን የእልቡር

ካሜረር መጽሐፍ ያረጋግጣል (1) ። ይኸው መጽሐፍ ከዚሁ አያይዞ ሶሊማን ከስ
ዌዝ ተዘጋጅቶ ወደ ሕንድ ለመዝመት ሲነሣ የመርከቡ ቍጥር ፸፫ ሲሆን ከነዚሁ
አራቱ በጣም ያማሩ ፤ የቀሩት እንደነገሩ መሆናቸውን የጦር መርከበኛው ቍጥር
እስከ ፯ሺ እንደሚደርስ ያመለክታል (2) ።

የጦር መርከቡ እንደ አው. ቀ. ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. ከስዌዝ ተነሥቶ
ከኻያ ቀን ጉዞ በኋላ ጅዳህ ደረሰ ። ከዚያ እግረ መንገዱን የየመንን ባላባቶች እያስ
በረና ስንቁን እያሰበሰበ ከየመን አልፎ አደን ወደብ ገባ ። አደንን በዚህ ጊዜ ከአ
ባቱ ከአብድል ዋሐብ ጣሂር ለጥቆ የሚገዛው ልጁ አሚር ኢብን ዳውድ ይባል
ነበር ። በሶሊማን ፓሻ የሚመራው የጦር መርከብ አደን ወደብ ላይ ሲቆም አሚር
ኢብን ዳውድ አራት መኳንንቶቹን ወደ መርከቡ ልኳቸው ስለነበረ ሶሊማን መኳ
ንንቱን በመልካም ዓይን ተቀብሎ ለያንዳንዳቸውም የልብስ ሽልማት ሰጥቶ ወደ
ጌታቸው ተመልሰው «ያለ ምንም ፍርሃት ወደ መርከቡ መጥቶ እንዲገናኘው»
ላካቸው ። እነሱም ሄደው ከነገሩት በኋላ መስፍኑ ዓረብ «የሚያስፈልገውን ያህል
ለመርከቡ ስንቅ ለመስጠት የተዘጋጀሁ ነኝ ወደ መርከቡ ላይ ለመውጣት ግን አይ
ሆንልኝም» የሚል ፍርሃት ያለበት አጠራጣሪ መልስ ሰጠ ።

በዚህ ጊዜ ኃይለኛው ሶሊማን በዚህ መልስ ተናዶ የጦር መርከበኞቹ መሣሪያ
ቸውን ይዘው ከመርከብ እንዲወርዱ አዞ ቀጥሎም «በቶሎ ወደ መርከቡ መተዳ
ለታላቁ ጌታ (ለቱርኩ ሱልጣን) መገዛትህን ከአላመንህ አደጋ ያገኝሃል» የሚል
የማስፈራሪያ ቃል ላከበት ። ይኸን ቃል ሲሰማ አሚሩ ብዙ ባለሟሎቹን አንዳሰለ
ተለ እሺ ብሎ ወደ መርከቡ ወጥቶ ከሶሊማን ፓሻ ጋር ተገናኘ ። ፓሻውም አሚሩ
በመግባቱ ተደስቶ በመልካም ዓይን ተቀብሎ ሲያነጋግረው ቆይቶ በስጦታም የአ
ስደሰተ መስሎ ከአሰናበተው በኋላ ከመርከቡ ወርዶ ከባሕሩ ጠረፍ ሲደርስ ሌላ
ትእዛዝ ለወታደሮቹ ሰጥቶ አሚሩን ከአራት የቅርብ ባለሟሎቹ ጋር አሰቅሎ አስገ
ደለው ።

እንባቢ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደሚያስታውሰው የቃጅማው ተክለ ሃይማኖት
ከአቡበከር ቀጭኑ ጋር ተዋግቶ ከተማረከና ከግራኝ ፊት ከቀረበ በኋላ ግራኝ ከነ
ጉሡ ከልብነ ድንግል የምትዛመደውን ሚስቱን ለራሱ አግብቶ ምርኮኛውን ተክለ
ሃይማኖትን ለአደኑ ሱልጣን ላከው ብሎ ዓረብ ፋቂህ ያረጋግጠው ለዚህ አሁን በስ
ቅላት ለተቀጣው ለአሚሩ መሆን አለበት ። ምናልባትም ላባቱ ለአብድል ዋሐብ
ጣሂር ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ሁለቱም ለግራኝ መሣሪያና ወታደር እየላኩ የክርስቲ
ያኑን ጦር ያስደበደቡ ናቸው ። ተክለ ሃይማኖት በሕይወት ኖሮ ይኸን ተአምር
ዓይቶ ይሆን ? ። የሆነ ሆኖ ሶሊማን ፓሻ ፭፻ ወታደሮች ወደ ከተማው ልኮ የአደንን
የወደብ ከተማ በቱርክ ቍጥጥር ውስጥ እንድትተዳደር ካደረገ በኋላ የሶሊማን መር

(1) ሬኔ ባሴት የፍቱሕ አል ሐበሽን በፈረንሳዊ ከተረጐሙበት ላይ ስልብ ብለዋል ገጽ 159

(2) አንድ ስሙ ያልታወቀ የቬኒዚያ ተወላጅ በዚሁ በጦሩ መርከብ ላይ የነበረ የጻፈውን መሠረት
በማድረግ አልበር ካሜረር የጻፈው La mer rouge ......... ገጽ 73 - 80

ከብ ከአደን ወደብ ተንቀሳቅሶ ወደ ሐድራሞት ደረሰ ። በዚያም ባለ ባለፉት ዓመታት (፲፭፻፴፭ - ፴፮) የፖርቱጋል መርከበኞች በዚሁ አቅራቢያ በሲሀር ከዓረቦቹ ጋር ተዋግተው ፴ የሚሆኑ መርከበኞች አምልጠው ከነመርከባቸው ወደ ምጥዋ ደርሰው ለንግሥት ሰብለ ወንጌል ገብተው ሲድኑ ፩፻፳ የሚሆኑት መርከበኞች በዚሁ በሐድራሞት በምርኮ ይኖሩ ነበርና የሰፈሩ ሼክ በዚህ ጊዜ ለሶሊማን ፓሻ አስረከባቸው ሲል የካሜረር መጽሐፍ ሜንዴዝ ፒንቶ ከጻፈው ላይ በመገልበጥ ያመለክታል (1) ።

ነገር ግን እንደ አው. ቀ፦ጥር በ፲፭፻፴፭ ወይም በ፲፭፻፴፮ ዓ. ም. ከዚህ ከሲሀር ያመለጡት ፖርቱጋሎች ምጥዋ ደርሰው በምን አኳኋን ከዚያ አልፈው ወደ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ደርሰው ባሽከርነት ለማገልገል እንደቻሉ አይታወቅም ። በዚህ ጊዜ እንደ ኢት. ቀ፦ጥር ፲፭፻፲፱ እና ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. (፲፭፻፳፯ - ፲፭፻፵፫) ግራኝ አህመድ ዓፄ ልብነ ድንግልንና የጦር አለቆቻቸውን አሸንፎ እርሳቸውንም በያለበት እያሳደደ ዕረፍት የነሣበት በየአውራጃው የራሱን ሹማምንት በሹመት ደልድሎ እርሱ ራሱ ለመቀመጫው ደንቢያን መርጦ በመቀመጥ ከድል አድራጊነት ያገኘውን ተድላና ደስታ በመዝናናት የሚያጣጥምበት ዓመት ስለሆነ በምን አኳኋን ከሐድራሞት ያመለጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ያንን ሁሉ ባሕርና በረሃ አልፈው ወደ ስደተኛዪቱ ንግሥት እንደመጡ አይታወቅም ። በዚህም ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል በሕይወት ስላሉ እርሳቸውን አልፈው ለንግሥቲቱ መግባታቸው ሁሉ አጠራጣሪ ስለሆነ በዚህ ረገድ ሁኔታው ሙሉ እምነት ሊጣልበት አይችልም።

የሆነ ሆኖ ሶሊማን በአለፈው እንደተመለከትነው የየመንን የአደንን የሐድራሞትን ባላባቶች እሺ ያሉትን እያሳመነ እምቢ ያሉትን ወይም እንደ አደኑ መስፍን እንደ አሚር መግባት ያንገራገሩትን በጭካኔ እየገደለ አልፎ ከሥር ከመሠረቱ ሊዋጋ ወደመጣበት ወደ ዲው ወደብ እንደ አው. ቀ፦ጥር መስከረም ፫ ቀን ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ደረሰ ።

ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ዲው በሰሜናዊ ሕንድ በመስቃት ትይዩ በጋምባያ አውራጃ ውስጥ የምትገኝ ወደ ባሕር ገባ ያለች የወደብ ከተማ ናት ። እርሷንም እንደ አው. ቀ፦ጥር ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ላይ ፖርቱጊዞች ይዘው መሽገው እንደተቀመጡባት ነው ። ስለዚህ አሁን በዚች ከተማ የቱርክ ጦር ከተማዋን ከቦ እየወጋ ለማጥፋት ትንሽ ሲቀረው ተሸንፎ እንደተመለሰ እንመለከታለን ።

(1) La mer rouge ......... ገጽ 78

## ምዕራፍ ፲፮

### በዲው ወደብ ላይ የሶሊማን ፓሻ ተሸንፎ መመለስ - ሲሄድና ሲመለስ በየመንገዱ በዓረቦች መሳፍንት ላይ የሠራው ግፍና የራሱ ፍጻሜ ።

ሶሊማን ፓሻ መስከረም ፫ ቀን ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. በዲው ወደብ በደረሰበት ዓመት በሕንድ የፖርቱጋል የንጉሥ እንደራሴ የነበረው ኑኖ ደ ኩንሃ ይባላል ። በርሱ ውስጥ ለፖርቱጋል መንግሥት ገባርነቱን አምኖ የሚያስተዳድረው ሃይማኖቱ እስላም የሆነው ሕንዳዊው የጋምቢያ ንጉሥ አለ ። እርሱ ደግሞ በበታቹ ዘሩ ኢጣልያዊ የሆነ የክርስትና ሃይማኖቱን በእስላምነት ስሙን ሳይቀር ወደ ዓረብኛ ለውጦ ኮጃ ዛፋር ተብሎ ወደቡንና ከተማውን ያስተዳድር ነበር ። ይህ ሰው ከብልጣቱ የተነሣ አንድ ጊዜ ለቀጥተኛ ጌታው ለጋምቢያ ንጉሥ ታማኝ እየመሰለ ባንድ ወገን ከፖርቱጋሎቹ ጋር እንደዚሁም አሁን ለውጊያ ከመጣው ከቱርኩ አዝማች ጋር በየመሥመሩ በማታለል ውስጡን ለሦስቱም ክፍሎች የሚታመን እየመሰለ የአድር ባይነት ጠባዩን በተግባር ያሳይ ነበር ይባላል ።

ከፖርቱጋሎቹ ወገን ባገረ ገዥው ሥር ሆኖ የወደቡ ምሽግ አዛዥ ፓቼኮና ምክትሉ አንቶኒዎ ደ. ሲልቬይራ ይባላሉ ። እነዚህ ሹማምንት ከነጦራቸው ከውስጥ ሆነው ሲከላከሉ ከውጭ ደግሞ የሶሊማን ጦር ከቦ ሲዋጉ ሁለቱም ወገኖች ሳይሸናነፉ አምስት ሳምንት አሳለፉ ። በዚህ መካከል የቱርክ መድፍ የምሽጉን ግንብ እየመታ ሲያፈራርስ ከፖርቱጋሎቹ በኩል የተተኰሰው ደግሞ የቱርኮቹን መርከቦች ሲጐዳ ሰነበተ ፤ ነገር ግን በሚያሳዝን አኳኋን ባንደኛው ቀን በተደረገው ጦርነት መሪው ፓቼኮ ተማረከ ። ሌሎቹ ፖርቱጋሎች ዋናው አገረ ገዥ (የንጉሡ እንደራሴ) ካለበት ከጐአ እርዳታ ይመጣልናል እያሉ እየተጠባበቁ ሲዋጉ ሶሊማን ፓሻ ብልጡን ሹም ኮጃ ዛፋርን ባጠገቡ አድርጎ ባንድ ወገን በብርታት እየተዋጋ በሌላ በኩል ደግሞ ከምሽጉ እየወጡ እጃቸውን ለሚሰጡት ምሕረት አደርጋለሁ እያለ የማታለል ፕሮፓጋንድ ሲያደርግና ፖርቱጋሎቹ ከመካከላቸው አንዳንዱ እየከዱ ከምሽጉ መውጣት ዠምሮ ተስፋ ሲቆርጡና እጃቸውን እስከ መስጠት እያሰቡ በሚጨነቁበት ሰዓት ከጐአ ወገን የሚጠብቁት እርዳታም ሳይመጣላቸው ከአውሮፓ ከፖርቱጋል መንግሥት ለእንደራሴነት የሚመጣው ዶም ጋርሺያ ደ. ኖሮንሃ የሚባለው አዲስ ጦር በመርከብ እንደያዘ መምጣቱ ተሰማ ።

በዚህ ጊዜ የጭንቁ ሁኔታ ከተከበቡት ፖርቱጊዞች ላይ ተነሥቶ ወደ ከባቢዎቹ ቱርኮች ላይ ተዛወረ ማለት ነው ። ባጠገቡ ያለው ዛፋርም የቀሩትም የጉዘራትና የሌሎቹም ወረዳ የሕንድ እስላሞች የጠበቀውን ያህል ስለአልተባበሩለት ገና ከአውሮፓ የደረሰው መርከብ ወደርሱ ተጠግቶ ውጊያ ሳይዠምር ሶሊማን በሌሊት ከመርከብ ወርዶ የብስ ይዞ ይዋጋ የነበረውን ወታደሩን በሙሉ ወደ መርከብ መልሶ ካሰፈረ በኋላ እንደ አው. ቍጥር ኅዳር ፮ ቀን ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. ሌሊቱን ከቢውን ጥሎ ወደመጣበት ተመለሰ ። ሲመለስም የተማረከውን ፓቼኮንና ሌሎችንም የፖርቱጋል ምርኮኞች እንደያዘ ነው ።

ለርዳታ በድንገት የደረሰው አዲሱ የጋርቺያ ደ. ኖሮንሃ ጦር ደግሞ ሶሊማ ንን ለመውጋት ሳይደፍር በቀጥታ ዲውን በሩቁ አልፎ ወደ ጐአ ዘለቀ ። ይኸውም የቱርኮቹን ጦር በመፍራት መሆኑ ነው ። በበኩሉ ሶሊማንም የጋርቺያን ጦር በመ ፍራት የከቢውን ጦርነት ትቶ የማምለጥ ያህል ወደመጣበት ተመለሰ ። በውስጥ የሚከላከለውም ጦር ርዳታ አጥቶ በጣም ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ በተጨነቀ በት ሰዓት የሶሊማንን ውጊያ ትቶ መመለስ እንደ አንድ ተአምራት ነው የቆጠ ረው ። የሶሊማንንና የጋርቺያ ሁኔታ በመጠኑ በኢትዮጵያ በ፲፱ነኛው መቶ ዓመት የደረሰውን የደጃች ውቤንና የራስ ዓሊን ጦርነት ይመስላል ። ሁለቱም ከተዋጉ በኋላ የተሸነፉ መስሏቸው ራስ ዓሊ ሲሸሹ ደጃች ውቤ እጃቸውን ሊሰጡ የመጡት የራስ ዓሊ ጭፍሮች እርሳቸውን ለመማረክ የመጡ መሆናቸውን በማመን እጃቸ ውን በቀጥታ ለነርሱ ሰጥተው ተማረኩ ። በዚህ ዓይነት ማራኪው ተማራኪ ሆኑ ። ድሉ የኛ ነው ለካ ብሎ ለመንገር ለራስ ዓሊ ለመንገር የተላከው መልከተኛ ራስ ዓሊን ከሸሹበት ለማግኘት ተቸግሮ ነበር ይባላል ።

የሆነ ሆኖ ጋርቺያ በጐአ ሆኖ የእንደራሴነቱን ሥልጣን ይዞ መርከብና ወታ ደር መልምሎ ወደ ዲው ለመጓዝ ባሰበበት ሰዓት ሶሊማን ጦርነቱን አቋርጦ ወደ መጣበት ተመለሰ የሚል መልእክት ከዲው ተከላካዮች ዘንድ ደረሰው ። ስለዚህ በጥር ወር ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. ከጐአ ወደ ዲው ሄዶ የፈራረሰውን ምሽግ መልሶ አሠ ርቶ ከጋምባያ ንጉሥና ከብልጡ ከኮ[illegible]ር ጋር በስምምነት ገዥነቱን አጽድቆ ወደ ጐአ ተመለሰ ።

ሶሊማን ፓሻ ከዲው በመጣበት መንገድ ተመልሶ ወደ አገሩ ሲገባ በቀድ ሞው የከፋት ጠባዩ ላይ የመጣበት ዓላማ ሳይሳካለት በመቅረቱ ከብስጭት የተ ነሣ በምርኮኞችና በሰላማውያን የሃይማኖት ወገኖቹ ላይ የሠራው ግፍ የበረከተ መሆኑን ወደፊት እናነባለን ። ከዲው ተነሥቶ ሐድራሞት ከደረሰ በኋላ ሺሀር ወደብ ላይ ቆሞ የወደቡን ምሽግ ቀድሞ በተዋቸው ወታደሮች ላይ ሌላ ፱፻ ጨምሮ የወደቧ ከተማ ለቱርክ ግዛት የጸናች ሆና እንድትቆይ አድርጎ ከዚያ ወደ አደን በሚጓዝበት ጊዜ በፊተኛው ጉዞው ጊዜ የአደኑን መስፍን አሚሩን ካሰቀለ ወዲህ ኮጃ ሙሐመድ (ዓሊ ኢብን ሶሊማን) የሚባል ተነሥቶ በዙሪያው ያለውን አገር በሥልጣኑ ውስጥ ካስገባ በኋላ በወደቡ ሶሊማን ፓሻ የተዋቸውን ወታደሮች በሰ ይፍ በትር አስፈጃቸው ።

ይኸንንም በማድረጉ ከቱርክ መንግሥት በተለይም ከሶሊማን ፓሻ የሚደር ስበትን በቀል በመገንዘብ ከፖርቱጋል መንግሥት ሹማምንት ጋር ለመቀራረብ በሚፈልግበት ሰዓት ፓዮ ደ. ኖርንሃ ( Payo de Noronha ) የሚባለው በባብኤል መንደብ በኩል ያንድ ክፍል ጦር ይዞ በሚጓዝበት ጊዜ በአደን ዓረቦቹ በቱር ኮቹ ላይ ያደረጉትን ሁሉ ስለሰማ በግሥጋሤ ወደ አደን ሄደ ። ኮጃ ሙሐመድም ፖርቱጋሉን በደስታ ተቀብሎ ተስማማ ። ይሁን እንጂ የቱርኮቹን በቀል በመፍ ራት ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ የፖርቱጋሉ መኰንን ፓዮ አደንን ለቆ ስለሄደ ሶሊ ማን ሲመለስ አደንን ይዞ በእጁ አደረገ ። የኮጃ ሙሐመድም ፍጻሜ አልታወቀም ።

ሶሊማን ፓሻ ከአደን በባብኤል መንደብ አልፎ ሞካ ሲገባ የሶሊማንን እያ
ዝና ጭካኔውን በመፍራት የየመን ሕዝብ ከነመሪው ገባለት ። ቀጥሎ አህመ
(ናኮዳ ሐሜድ) ለሚባለው ለዘቢድ መስፍን ቢልክበት መልካም ንግግርና ለስን
የሚሆን ገጸ በረከት እየላከ እርሱ በማመንታት ወደ ኋላ ዘገየ ። በዚህ ጊዜ ሶሊማ
ከነጦሩ ከመርከብ ወርዶ ወደዘቢድ ከተማ ሲጓዝ ብዙ ሰው ከአህመድ (ነጅው?)
እየከዳ ገባለት ። በዚህ ጊዜ መከረኛው አህመድ ብዙ ሰው እንደከዳው ሲያውቅ
በግድ በጦር ተማርኬ ከመያዝ ራሴ አምኜ ብገባ የምህረት ተስፋ ይኖረኝ ይሆናል
በማለት በአንገቱ ገመድ እንዳሰረ የካቲት ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. እንደ አው.
ቆጥር ከሶሊማን ፊት ቀርቦ «ባርነቴን ለታላቁ ጌታ (ለሱልጣን ሶሊማን የቱርኩ
ንጉሠ ነገሥት) እንድም ቀን ለማጓደል እንዳላሰብሁ አላህ ምስክሬ ነው» ብሎ
ማለ ። ግፈኛው ሶሊማን ግን ከምሕረትና ከርኅራኄ ጋር በፍጹም ስለማይተዋወቁ
ወዲያው አንገቱን በሰይፍ አስቀርጦ አስገደለው ።

በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ ከሶሊማንና ከጦሩ ፊት እየሸሸ ወደየተራራው እየሄደ ከተ
ደበቀ በኋላ «ምሕረት አድርጌያለሁና ሁሉም ያለፍርሃት ወደየቤቱ ይመለስ»
የሚል አዋጅ አስነግሮ ነበር ። ነገር ግን የአዋጁን ተስፋ በመጠራጠር ብዙ ሰው
ወደ ኋላ በዘገየበት ሰዓት በዚያ የሚኖሩ ቍጥራቸው እስከ ሁለት መቶ የሚደርስ
በጉብዝናቸው የታወቁ የሀበሻ ተወላጆች በአዋጁ ቃል ተማምነው ከገቡለት በኋላ
እያሳሳቀ በፈገግታ ተቀብሎ በሠራዊቱ ውስጥ ስማቸው በወታደርነት እንዲመዘ
ገብ አደረገ ። ቀጥሎ መሣሪያቸውን እየተዉ ቀርበው እጁን ይሳሙ ብሎ መሣሪያ
ቸውን ካስጣላቸው በኋላ ወደ አንድ ቅጥር ውስጥ ይግቡ ብሎ ባዶ እጃቸውን ካስገ
ባቸው በኋላ ሁሉንም በሰይፍ አስደብድቦ አስፈጃቸው (1) ። እነዚህ አበሾች ቀደም
ብሎ በፈቃዳቸው እንጀራ ፍለጋ የሄዱ የቀሩትም በግራኝ ጦርነት እየተማረኩ ለዘ
ቢድ ፓሻ የተላኩ ሳይሆኑ አይቀሩም ።

በዘቢድ ከተማ ውስጥ ይኸን የመሳሰለውን ግፈኛ ተግባር ከፈጸመ በኋላ ለከ
ተማው ጥበቃ ፩ሺ ወታደር ትቶ ጉዞውን ለመቀጠል ወደ መርከቡ ተመለሰ ። ከባ
ሕሩ ጠረፍ በደረሰ ጊዜ ከዲውና ከሺህር ከሌላም የጦር ግንባር ተማርከው ከርሱ
ጋር ይጓዙ የነበሩትን ፩፻፵፮ የፖርቱጋል ተወላጆች በመርከቡ አጠገብ እያንዳንዳ
ቸውን ለወታደሩ አከፋፍሎ ባንድ ምልክት ሁሉንም ጭንቅላታቸውን ባንድ ጊዜ
እያስቆረጠ አስገደላቸው ።

በዲው ወደብ ሲከላከል የተማረከውን የፖርቱጋል የጦር መኰንን የፓቼኮ
ንና የጓደኞቹን ጭንቅላት አፍንጫና ጆሮአቸውን አስቆርጦ በጭንቅላታቸው
ውስጥ ገለባ አስሞልቶ ወደስጣንቡል ለቱርኩ ሱልጣን ላካቸው ይባላል ።

እንደዚህ አድርጎ ጨካኙ ሶሊማን ከዘቢድ ወደ የመን ተጉዞ በሰናዓ ደርሶ የሰ
ናዓውን ይማም ሸሪፍ ኤድ ዲን የሚባለውን እንዲገባ ላከበት ። ይማሙ ግን ሶሊ

(1) La mer rouge première Partie.......... ገጽ 84 - 85

ማን ባለፈው የሠራውን ሁሉ ስለሚያውቅ በሰናዓም ካየሩና ካገሩ መጥፎነት የተ ነሣ ብዙ ጊዜ ለመቆየት እንደማይችል በመገመት ፈጽሞ ሳይገባለት በመቅረቱ ሕይወቱን አዳነ ፡፡ ሶሊማንም ሙስጠፋ የሚባለውን በርሱ እግር ለየመን ሾሞ ወደ ጀዳህ ጉዞውን ቀጠለ ፡፡ በዚያም ደርሶ በሜካ ትንሽ ጊዜ ከቆየ በኋላ ጉዞውን ቀጥሎ በሄደ በ፲፩ኛው ወር ተመልሶ ስዌዝ ገባ ፡፡ ከዚያም ወደ ስጣንቡል ሄዶ ለዋናው ሱልጣን የዓረብን ግዛት አደላድሎ መምጣቱን ብቻ ሳይሆን በሕንድ ተሸንፎ የተ መለሰበትን የዲውን ጦርነት እንዳሸነፈ አስመስሎ በማስረዳትና በግፈኛ ሥራው በመመካት ትንሽ ጊዜ ወዚር እየተባለ የጡረታ አበል እያገኘ ከቆየ በኋላ ሥራውና በዲው መሸነፉም እያደር ስለተገለጠበት ከማዕርጉ ተዋርዶ ተግዞ ሳለ ወዲያው ለሕይወቱ ጭምር በመስጋት ወደ ተወለደበት አገር ሸሽቶ ሄዶ እንደተቀመጠ በሄጅራ አቈጣጠር ፱፻፷ ዓመት (፲፭፻፶፪ - ፶፫ እንደ አው. ቀ.) ራሱን በገዛ እጁ ገድሎ ሞተ ሲል አልቤር ካሜረር ከቬኒሲያው ጸሐፊ ተርጉሞ በፈረንሳዊኛ በዚህ ዓይነት ይተርካል ፡፡

ሶሊማን ፓሻ የቱርክ ሱልጣን እንደራሴ በፊተኛው ጊዜ ይኸውም ማለት ከዓፄ ይኵኖ አምላክ ዘመን ዠምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ በግብፅ የማመሉክ ሱልጣኖች ሥር ሲተዳደሩ የነበሩትንና በኋላ ደግሞ ሱልጣን ሰሊም ግብፅን በ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. አስገብሮ አሁን እስከዘመተበት እስከ ፲፭፻፷፫ ዓ. ም. ድረስ ይነስ ይብዛ ከፖርቱጋል እየተከላከሉም ፲፪፱ሰማሙም በነፃነት የኖሩትን የዓረብ አገሮችን ነገሥታትና መሣፍንት የአውራጃ ግዛታቸውንና ወደባቸውን በተረጋገጠ አኳኋን እንዳስገበረ ተመልክተናል ፡፡

ሶሊማንም ለማስገበር ሲል በጭካኔና በእብሪት ማታለልንና ክዳትን እያፈራረቀ የፈጀውን ሰው በመጨረሻም የርሱን ፍጻሜ ተመልክተናል ፡፡ መቼም ይኸን የመሰለ የደም ሰው የሕይወቱ ፍጻሜ ሊያምር አይችልም ፤ እንዲያውም ለእንደ ዚህ ያለው ግፈኛ መሪ በግዞት ኖሮ በመጨረሻ ራሱን በመግደል ሕይወቱ ሲያቋርጥ ለፍዳው ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም ፡፡

በዚህ መካከል የምንመለከተው እነዚህ ሁሉ የአደን የዘቢድ የሞካና የሐድራሞት የጀዳ የዓረብ መሳፍንት በተለይ የዘቢዱና የአደኑ የግራኝ አህመድን ወረራ በመደገፍ ከየአገራቸው ቀይ ባሕርን እያቋረጠ ወደ ግራኝ እየመጣ ካፄ ልብነ ድንግልና ከጦራቸው ጋር የሚዋጋውን ምልምል ጦር መሣሪያ እያስታጠቁ ስንቅ እየሰጡ ኢትዮጵያን በየጦሩ ግንባር ያስጠቁ ናቸው ፡፡ ለዚህም ውለታቸው ባለፉት የጦርነት ምዕራፎች እንዳነበብነው ግራኝ አህመድ ከወዲህ ከኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ከየአብያተ ክርስቲያኑና ከየገዳማቱ ከደብረ ሊባኖስ ከነመካነ ሥላሴ ከሌሎቹም የተዘረፈውን የወርቅና የሐር ልብስ ምርኮኛ ጭምር እየላከ አክብሮአቸዋል ፡፡ የንጉሡ ልጅ ሚናስ ከጦርነቱ ላይ ተማርኮ የተላከው አሁን በሶሊማን ፓሻ እጅ ለተገደለው አንዳንድ ጊዜ ፖርቱጋሎች ወናኮዳ ሃመድ ለሚሉት ለአህመድ ነው ፡፡ ባለፈው እንዳነበብነው የቃጅማው ተክለ ሃይማኖት ከውጊያ በአቡበከር

ቀጭኑ ተማርኮ ካዔ ልብነ ድንግል የምትዛመደውን ሚስቱን ግራኝ ለራሱ አስቀርቶ እርሱን ለአደን መስፍን እንደመታያ የላከውን እናስታውሳለን ። ይኸም ሰው በአሁኑ ሶሊማን ፓሻ በዘመተበት ጊዜ በሕይወት ይኑር ወይም ከነዚያ ከተገደሉት ከ፳፻ አበሾች ጋር አብሮ ይገደል አይታወቅም ።

ቀድሞ ባዔ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ ካዔ ልብነ ድንግል ወደ ካይሮ የተላኩትን ፳፻ መልክተኞች በመጥፎ አኳኋን የተቀበላቸው የመልክተኞቹ መሪ ኢትዮጵያዊው መስፍን በፊቱ ይዞ በመጣው ወንበር ላይ እንዳይቀመጥ የከለከለው ፤ የቀረበለትን ገጸ በረከት ዝቅተኛ ነው በማለት «ከፊቴ አንሱ» ብሎ አቅራቢውን የተሳደበው ሱልጣን አል ጋውሪ ከቱርኩ ሱልጣን ከሰሊም ፩ኛ ጋር ሶርያ ውስጥ ሲዋጋ መሞቱን የርሱ ተከታይና ዘመዱ ቱማን በካይሮ ተዋግቶ ከተሸነፈ በኋላ ከሸሸበት ባላገር ይዞ ላሸናፊው ለሰሊም አቅርቦት በሱልጣኑ ትእዛዝ በካይሮ በባብዙይለህ በር ላይ ተሰቅሎ መሞቱ ፤ አሁን ደግሞ የነዚህ የዓረብ መሳፍንት በሶሊማን ፓሻ እጅ በጭካኔ መሞታቸውን ስንመለከት እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አንዳንድ ጊዜ በጠላቶቿ በዓረቦቹ ሲያስጠቃት ጠላቶቿን የዓረብ አገሮችን መሳፍንት ደግሞ በሃይማኖት ወገኖቻቸው በቱርኮች ሲቀጣቸው ይታያል ፡ ግራኝ አህመድ ግን በበኩሉ በኢትዮጵያ የዠመረውን ወረራ ለማቃናት ቀድሞ ከዓረቦቹ ጋ[illegible]የነበረውን የወዳጅነት ግንኙነት አሁንም ከቱርኮች ጋር እንደያዘ ነው ።

የሆነ ሆኖ ሶሊማን በዚህ ዓይነት ከስዌዝ ተነሥቶ ወደ ዲው ዘምቶ የዲውን ወደብ ደብድቦ እንደተመኘው ፈጽሞ ማፈራረስ ባይሆንለትም የዓረብ ነክ የሆኑትን አውራጃዎች ለቱርክ ሱልጣን አስገብሮ ከተመለሰ በኋላ በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ላይ ደግሞ ፖርቱጋሎች የዚህን ብድር ለመመለስ የጦር መርከብ አዘጋጅተው ከጐአ መጥተው ስዌዝን ሲደበድቡ በዚህም ጊዜ ቍጥራቸው ከ፬፻ በላይ የሆነ የፖርቱጋል ወታደሮችን በምጥዋ በኩል አውርደው ባባታቸው እግር የተተኩት ዓፄ ገላውዴዎስ የፖርቱጋሎቹን ርዳታ ይዘው ግራኝ አህመድን አሸንፈው መንግሥታቸውን ሲያቋቁሙ ወደፊት በየምዕራፉ እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፻፯
## የእስጢፋኖስ ደጋማ ከጐአ ወደ ስዌዝ መዝመት (፲፭፻፴፫ የካቲት - ግንቦት)

ሶሊማን ፓሻ እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ከስዌዝ ተነሥቶ በቀይ ባሕርና በአደን ሰላጤ በሕንድ ውቅያኖስ ዳር የሚገኙትን ወደቦች እያስገበረ የፖርቱጋል የጦር መርከብ የሠፈረበትን የዲውን ከተማ በመድፍ ደብድቦ ፈጽሞ የመደምሰሱ ጉዳይ ሳይሳካለት ቀርቶ ወደመጣበት እንደተመለሰ አሁን ደግሞ በሦስተኛው ዓመት በሕንድ የፖርቱጋል ጠቅላይ ገዥ እስጢፋኖስ ደጋማ ባንድ ወገን የዚህን አጸፋ በቱርክ ላይ ለመመለስ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ

ዓፄ ልብነ ድንግል የሚጠብቁትንና ስለዚሁ ቤርሙዴዝ የተላከበትን የጦር ርዳታ ወደ ምጥዋ ለማድረስ ሲዘጋጅና ሲዘምት በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን ። ከዚህ ዘመቻ የግራኝ ጥፋት የኢትዮጵያ ደኅንነት ይወለዳል ።

የቱርክ ጦር በዲው ወደብ ላይ በዘመተ ባመቱ በ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. በሊስቦንና በሮማ ጳጳሱንና ንጉሡን ወደ ኢትዮጵያ ርዳታ እንዲልኩ ደጅ ሲጠና የነበረውን ቤርሙዴዝንና ያገሩን ጉዳይ ችላ ብሎ በሊስቦን ፲፪ ዓመታት ሙሉ የዘገየውን ጴጋ ዘአብን የያዘው በፔሮ ሎፔዝ የሚታዘዘው መርከብ ሕንድ ደረሰ ። የኢትዮጵያን ሥቃይና መከራ ባገሩ ላይ ሆኖ ብዙ ዓመታት የተመለከተው ቤርሙዴዝ የሄደ በት ጉዳይ ተከናውኖለት ለኢትዮጵያ ርዳታ እንዲላክ የሚለውን ንጉሣዊ ትእ ዛዝ ከእስጢፋኖስ በፊት አገረ ገዥ ለነበረው በዲው ጦርነት ሰዓት ወደ ሕንድ ለደ ረሰው ለኖሮንሃ ይዞ ነበር ።

ቤርሙዴዝ ከአገረ ገዥው ከኖሮንሃ ጋር በመስማማት ከሕንድ አገር ወደ ምጥዋ መላከተኛ እየላኩ የኢትዮጵያን ሁኔታ ሲያሰልሉ መሰንበታቸው ኢትዮጵ ያም በዚህ ጊዜ ፈጽማ በግራኝ አህመድ ሥልጣን እጅ መውደቋ ፤ በዚሁ መካከ ልም እላይ እንዳልነው ቱርኮች እንደገና ከዲው ዘመቻ ወዲህ ሌላ ዘመቻ ለማድረግ በስዌዝ የጦር መርከብ ያዘጋጃሉ የሚሉ ወሬ አብሮ ስለመጣ ለዚሁ ለሁለቱ ጉዳይ መርከቡንና ተዋጊ ወታደር ከስንቅ ጋር ከያለበት መሰብሰብ እንደዠመረ በመካ ከሉ በዚሁ ዓመት (፲፭፻፴) ስለሞተ 1538 እግር በሕንድ የንጉሥ እንደራሴነቱ ሥፍራ ለስመ ጥሩው ለቫስኮ ደጋማ ልጅ ለእስጢፋኖስ ደጋማ ተሰጠ ።

እርሱም የሹመት አባቱ የዠመረውን ዝግጅት በጥድፊያ ጨርሶ ፪ሺ ምርጥ ወታደሮች ከነሹማምንቶቻቸው ደልድሎ ካዘጋጀ በኋላ እነዚህን ቊጥራቸው እስከ ሰባ በሚደርስ ከብደታቸውና ፍጥነታቸው በተለያየ ልዩ ልዩ የጦርና የስንቅ መርከ ቦች እንደያዘ በታኅሣሥ ወር መጨረሻ ላይ ፲፭፻፴ ዓ. ም. (እንደ አው. ቀ.) የጐአን (ሕንድ) ወደብ ለቆ ከተጓዘ በኋላ ሶቆጥራ ደረሰ ። ከዚያም በአደን በኩል አልፎ በጥር ፳፩ ቀን ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ባብ ኤል መንደብን አልፎ በየካቲት ፰ ቀን ዳህላቅ ደሴት በየካቲት ፲ ቀን ምጥዋ ወደብ ደርሶ መልሕቁን ጥሎ ቆመ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ በበታቹ ካሉት የጦር መኰንኖች መካከል ክሪስቶፎሮስ ደጋማ የሚባለው ወጣትና ታናሽ ወንድሙ ያንድ ክፍል አዛዥ ሆኖ አብሮ ነበር ። እላይ እንዳልነው የዘመቻው ዓላማ ፩ኛው ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ፤ ሁለተኛው የቱር ክን ኃይል ለመስበር የታቀደ ከፍተኛ ጉዳይ ስለነበረ በዚህ መርከብ ላይ የተሣፈ ሩት ሁሉ ወታደሮቹም የጦር ሹማምንቶቹም ምርጥ እንደነበሩ በመርከቡ ላይ የነበ ረው ራሱ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ያረጋግጣል (1) ።

ከዚሁ እያይዞ መርከቡ ምጥዋ በደረሰበት ሰዓት እስጢፋኖስ ደጋማ የኢትዮ ጵያን ወሬ ሲጠያየቅ ከዚህ በፊት ጭምጭምታው የተሰማውን አሁን ግን በትክ ክል ዓፄ ልብነ ድንግል መሞታቸውን ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከልጆቻቸው

(1) Histoire du Christianisme-La croze ገጽ 103 - 104




እስጢፋኖስ ዳጋማ የሕንድ አገረ ገዥ የክርስቶፎርስ ዳጋማ ታላቅ ወንድም
(ከካሜረር መጽሐፍ)


አንዱ (ገላውዴዎስ) ከግራኝ አህመድ ጋር እየተከላከሉ መንግሥትን ሳይለቁ መቆየታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ከተነሡት ከሁለቱ መነኲሳት አንዱ አባ ዮሴፍ የሚባለው የብዙ ገዳማት አለቃ እንዳስረዳቸው ይገልጻል ፡፡ ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ጉዳይ የበለጠ የሚያሳስበው በቅድሚያ የቱርክን የጦር መርከብ የመደምሰሱ ጉዳይ ስለሆነ እስጢፋኖስ ደጋማ ምጥዋ ላይ ከበድ ከበድ ያሉትን መርከቦች በዘመዱ በአማኑኤል ደጋማ አዝማችነት ትቶ እንደዚሁም በትክክል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዲመረምር ከዚህ በፊት በ፲፭፻፳ ዓ. ም. ከነሮድሪግ ደሊማና ከነፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አገር የሚያውቀውን አሪያስ ዲያዝ የሚባለውን የፖርቱጋልና የሕንድ ክልስ ሌላም ሰው ጨምሮ በምጥዋ በኩል ወዳገር ውስጥ ከላከ በኋላ እስጢፋኖስ የመጣበትን ዓይነተኛ ዓላማ ለመፈጸም ይኸውም ማለት በስዌዝ ተሰብስበዋል የተባሉትን የቱርክን የጦር መርከቦች ለመደብደብ ከምጥዋ ጉዞውን ወደ ሰሜን ቀጥሎ በሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. የሲናይን ጠረፍ አልፎ በስዌዝ ትይዩ እንደቆመ እንደ ጠበቀው የቱርክን የበረከተ መርከብ ሊያገኝ አልቻለም ፡፡ የቱርክ መርከቦች ፊት ለፊት መግጠም ስለአልቻሉ ምሽጋቸውን ... ምፍራቸውን ለቀው ተበታተኑ ፡፡

ስለዚህ ከጦር ሹማምንቱ አንደኛው ጆአኦ ደካስትሮ የመሬት አቀማመጥና የመንገድ የአየር ሁኔታ መርማሪ የሆነው ቀደም ብሎ የወደቡን ከተማ ለመደብደብ የሚቻልበትን ሁኔታ እንዲያጠና የተላከው እንዳስረዳው የወደቡ ዳርቻ በተቆለለ አሸዋ የተከለለ በመሆኑ ወደቡን በመድፍ የመደብደቡ ጉዳይ እምብዛም አልተሳካም ፡፡ ቢቸግር በድፍረት ያንድ ክፍል ወታደሮች ከመርከባቸው ወርደው መሬት ይዘው ውጊያ እንደዠመሩ ከካይሮ ለርዳታ መጥተው ከሚጠባበቁዋቸው ከሁለት ሺ ወታደሮች ላይ ሳያስቡት ወድቀው ስለነበረ ከነርሱ ጋር በተዠመረው ውጊያ ያለቁት አልቀው የተረፉት በሽሽት ወደ መርከባቸው ተመለሱ ፡፡

ስለዚህ በ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. መዠመሪያ ላይ በዠኔራል ወሊንግተን የሚመራው የእንግሊዝ ጦር በምድር ላይ ጦርነት ናፖሌዎንን ማሸነፍ የናፖሌዎንም ጦር የእንግሊዝን ጦር በባሕር ላይ ማጥቃት እንዳልሆነለት የቱርክ የመርከብ ጦርም የፖርቱጋሎቹን መርከብ ፊት ለፊት ወግቶ መመለስ ስለአቃተው እስጢፋኖስ ደጋማም ያስከተለውን አነስተኛ ጦር ወደ የብስ አውርዶ የበረከተውን የቱርክ የእግረኛ ጦር መግጠም አደገኛ መሆኑን ለሙከራ በተላኩት በትንሾቹ ወታደሮች ስለተገነዘበው በጠቅላላው በስዌዝ ወደብ በሙሉ ፳፬ ሰዓት ያህል ከቆየ በኋላ በሚያዝያ ፳፰ ቀን መልሕቁን አስነሥቶ ወደመጣበት ወደ ምጥዋ ተመልሶ ግንቦት ፳ ቀን ደረሰ (1) ፡፡

እስጢፋኖስ ደጋማ ወደ ስዌዝ ዘምቶ ወደ ምጥዋ ከመመለሱ በፊት በነበሩት ትንሽ ቀናት ውስጥ በአማኑኤል ደጋማ ከሚታዘዘው መልሕቁን ለቆ ምጥዋ ከቆ

(1) La mer rouge-les Portugai et les Abissins devant l'Islam- A. Kammerer, ገጽ 95 - 132



መው ከትልቁ መርከብ ላይ ፷ የሚሆኑ ወታደሮች አለቃቸውን ሳያስፈቅዱ በትና ንሽ ጀልባዎች ተሳፍረው ከየብሱ ላይ መብልና መጠጥ ፍለጋ ወረዱ ። የወረዱበት ሥፍራ ደረቅ በረሃማ ከመሆኑ የተነሣ ከግራኝ ሹማምንት አንዱ አግኝቶ የያዛ ችሁትን የጦር መሣሪያ አስረክቡኝና የፈለጋችሁትን መብልና መጠጥ እሰጣችኋ ለሁ ብሎ ላይገድላቸውም ቃል ከገባላቸው በኋላ በረሃብና በጥም የተጎዳከሙት እነ ዚህ ወታደሮች ባንድ ወገን የሰጣቸውን ቃል በመተማመን ዳግመኛም ሸሽተው ለማምለጥም ለመዋጋትም አለመቻላቸውን በመገንዘብ መሣሪያቸውን ካስረከ ቡት በኋላ በመብልና በመጠጥ ፈንታ ሁሉንም በማስገደል ሞት ጋበዛቸው (1) ። የነዚህን ሟቾች ሁኔታ ካሚረር ለየት አድርጎ በመተረክ ቍጥራቸውንም እስከ ፩፻ ያደርሰዋል ። ከመርከብ የወረዱትም የኢትዮጵያ ሀብት አስጐምጅቷቸው እንደዚ ሁም በቶሎ ከክርስቲያኖቹ ጐን ተሠልፈው እስላሞቹን በቶሎ ለማጥቃት መሆኑ ንና ወዳገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ይህ አደጋ እንደደረሰባቸው ይተርካል (2) ።

የሆነ ሆኖ እስጢፋኖስ ደጋማ ወደ ቀይ ባሕር ስለመዝመቱ ስዌዝ ሄዶ የቱር ክን መርከቦች አጥቶ ስለመመለሱ ወንድሙ ክሪስቶፎሮስ ደጋማ ፬፻ የፖርቱጋልን ወታደሮች ይዞ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ተገናኝቶ ከግራኝ አህመድ ጦር ከመ ዋጋቱ በፊት በዚህ በቀይ ባሕርና በየወደቦቹ የተደረገውን ጦርነትና የክሪስቶፎሮ ስንና የወታደሮቹን ከግራኝ ጦር ጋር በጀግንነት የመዋጋታቸውን ታሪክ የሚነግ ሩን ደንበኛ የታሪክ ምንጮች ሁለት ናቸው። እነዚህም አንደኛው ከዚህ በፊት እን ደተመለከትነው ይኸው ቤርሙዴዝ የጻፈውና እንደ አው. ቍጥር ፲፯፻፴፱ ዓ. ም. ላክሮዝ የኢትዮጵያና የአርመን የክርስትና ታሪክ በሚል አርእስት ወደ ፈረንሳዊ ተርጉሞ ያሳተመው ። ሁለተኛው በመርከብ አብሮ መጥቶ ግራኝ እስኪሞት ድረስ ጉዞውንም ጦርነቱንም አብሮ የተካፈለው ሚጉኤል ደ. ካስታንሆዞ (MIGUEL DE CASTANHOZO)የሚባለው የፖርቱጋል ወታደር የጻፈው መጽሐፍ ነው ። ከሁለቱም አጻጻፍ የሚጉኤል ደካስታንሆዞ አጻጻፍ የበለጠ ሐቀኛና እውነተኛ መሆኑን ጸሐፊው ሁሉ ተገንዝቦለታል ።

ይህ የካስታንሆዞ መጽሐፍ ወደፊት እንደምናገኘው ካስታንሆዞ ግራኝ ከሞተ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ በፖርቱጋል ቋንቋ በፖርቱጋሎቹና በግራኝ አህመድ መካከል የተደረገውን ጦርነት የአዝማቹን የክርስቶፎሮስ ደጋማን ዠግንነትና ብር ታት በሰፊው የጻፈው በእንግሊዝኛና በኢጣልያንኛ ተተርጉሞ ሳለ በ፲፱፻፳ - ፮ ዓ. ም. እንደ አው. ቍጥር ስለአክሱም ሐውልት ምርመራ በብዙ የደከሙት ፕሮ ፌሰር ኢና ሊትማን የሚባሉት ሊቅ ወደ ጀርመንኛ ተርጉመው አሳተሙት ። ከጀ ርመንኛው ላይ ደግሞ ዶክተር ሙራድ ካሚልና አቶ ዮና ቦጋለ ወደ አማርኛ ተርጉ መው የፖርቱጋሎች ዠግንነት በሚል አርዕስት ታትሞ ወጥቷል ።

ነገር ግን ይህ መጽሐፍ በግራኝ አህመድና በፖርቱጋሎች መካከል የተደረ

(1) Histoire du Christianisme ገጽ 103 - 104
(2) La mer rouge 1er partie ገጽ 133

ገውን ጦርነት በሰፊው እየዘረዘረ ሲጽፍ ከወደ መዠመሪያው ላይ እስጢፋኖስ ደጋማ ወደ ቀይ ባሕር ለመዝመት በሕንድ ያደረገውን ዝግጅት በውቅያኖስ ባሕር ያደረገውን ጉዞ በቀይ ባሕር በተለይ ምጥዋ ወደብ እንደደረሱ የእስጢፋኖስን ወደ ስዌዝ ዘምቶ መመለስ ፰ (ወይም ፩፪) የሚሆኑት መርከበኞች እህልና ጣፋጭ ውኃ ፍለጋ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ይሁን በጀልባ ሄደው በእስላሞች መገደላቸውን አልጻፈውም ።

ስለዚህ ስለዋናው ጦርነት የካስታንሆዞ መጽሐፍ የተሻለ ሲሆን እስጢፋኖስ ደጋማ ምጥዋ ወደብ ከደረሰ በኋላ በቀይ ባሕር ዙሪያ ስለተደረገው ግጭት ሁኔታውን በመጠኑ የሚያመለክተን የዚሁ የዮሐንስ ቤርሙዴዝ መጽሐፍ ነው ። እነዚህን መጻሕፍት መሠረት በማድረግ ከዚያ ወዲህ የተነሡ የፖርቱጋልና የእንግሊዝ የፈረንሳዊና የጀርመን የኢጣልያና የመስኮብ ጸሐፊዎች በየመልኩ በየቋንቋው አስፋፍተው እየጻፉ አሳትመዋል ። እኔም ላሁኑ መጽሐፍ በመጠቀም ከነርሱ መካከል እገኛለሁ ማለት ነው ።

አሁን በሚቀጥሉት ምዕራፎች ክሪስቶፎሮስ ደጋማ ከ፬፻ ወታደሮች ጋር ሆኖ ስለክርስቲያናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት በምን አኳኋን ተዋግቶ እንደሞተ የተረፉትም ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ሆነው ግራኝን ተዋግተው በመግደል እንደረዱ እንመለከታለን ።

ISIC

## ምዕራፍ ፪፰

### የአርኪቆ (ድሆኖ) ወደብ መመታት - የኑር በጥይት ተመትቶ መሞትና ጭንቅላቱ ወደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል መላክ (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ግንቦት - ሰኔ)

የፖርቱጋል የጦር መርከብ ምጥዋ ገብቶ ለተጠቃው የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥት ፬፻ ወታደር ለጦር ርዳታ ሲልክ ይኸን ርዳታ ከመላኩ በፊት በየወደቡ ላይ የቱርክ የመርከብ ኃይል ከአገር ተወላጆቹና ለጊዜው አገሩንና ቀበሌውን ከሚያስተዳድሩት ከግራኝ አህመድ የጦር አለቆች ጋር በመተባበር የፖርቱጋሎችን ወታደሮች በኃይል ሳይቃወሙና በዚህ ቀበሌ የታወቀ ጦርነት ሳያደርጉ መቅረታቸው ትንሽ የሚገርም ነው ።

ምጥዋ ወደብ ፊት ለፊት የቆሙት የፖርቱጋል መርከቦች በውስጣቸው ያለው የጦር ወታደር እንዳይታወቅ ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው የጦር ርዳታ ከመርከቡ ወደ ወደቡ የሚወርደው በታላቅ ጥንቃቄና ምሥጢር መሆኑን የመርከቡም አመጣጥ ለንግድ የመጣ መሆኑን ለማስመሰል ብዙ ዘዴ መሥራታቸውን ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በጽሑፉ ገልጿል ። የዘዴውን አነጋገርና ተንኮለኞቹ እስላሞች በተንኮል የሚሸነፉበትንና የሚታለሉበትን ዘዴ ለዋናው መሪ በምክር ያስጠና የነበረ ራሱ መሆኑን በጽሑፉ ላይ ያመለክታል ።

በዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ልብነ ድንግል በሞቱበት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ላይ የግራኝ የባሕር ነጋሽ የነበረው ኑር መሆኑን ቤርሙዴዝ ሲገልጽ በበኩሉ ደግሞ ካስታንሆዞ ምጥዋ እንደገባን ባሕር ነጋሽ የሚባለው ከኢትዮጵያ ንጉሥ (ከገላውዴዎስ ይሆናል) ተልኮ ወደኛ መጣ ይላል (1) ።

ይኸውም ሁኔታ የሚያመለክተን በኢጣልያ የወረራ ዘመን (፲፱፻፳፰ - ፲፱፻፴፫ ዓ. ም.) ባንዱ የወረዳ ግዛት ላይ ወራሪው ኢጣልያ የራሱን ተወላጅ ኢጣልያን ወይም ለኢጣልያ ታማኝ መስሎ የሚያገለግለውን ኢትዮጵያዊ (ባንዳ) መርጦ ሲሾም የአርበኞቹ መሪዎች ደግሞ የራሳቸውን ወገን ሾመው ግብር ያስገብሩ እንደ ነበር ሕዝቡም የሚያደርገው እየቸገረው ለሁለቱም ይገብር እንደነበር በዚህም በግራኝ አህመድ ወረራ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ባንዱ አውራጃ ላይ አሸናፊው ግራኝ አህመድ የራሱን ሰው ሲሾም ተሸናፊው ዓፄ ልብነ ድንግል ወይም በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ ንጉሥ ዓፄ ገላውዴዎስ በትክክል ባይገዙም ሥርን መሠረትን ላለመልቀቅ በሌላው አውራጃ እንደሚሾሙት በዚህም በቀይ ባሕር ቀበሌ ግራኝ አህመድ ኑርን ባሕር ነጋሽ ብሎ ሲሾም በበኩላቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ወይም ልጃቸው ዓፄ ገላውዴዎስ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅን ሾመው ኖሯል ማለት ነው ።

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በመጽሐፉ ላይ የሕንድ አገረ ገዢ ከስዌዝ ወደ ምጥዋ ከተመለሰ በኋላ እነዚያ ስድሳ የፖርቱጋል ወታደሮች በከዳትና በማታለል በእስላሞቹ እጅ ከተገደሉ በኋላ ዋናው አገረ ገዥ [illegible]ፋኖስ ደጋማ ለመርከበኛው ስንቅ የሚሆን በሬና ላም ወኃም ጭምር ሺ በሚሆን የጥጥ ጨርቅ ገብይቶ ይመለስ ዘንድ አንድ መርከብ ወደ አርኪቆ መላኩን የግብይይቱ ጉዳይ ተፈጽሞ ከብቶቹን እየነዱ በየብስ ከአርኪቆ ወደ ምጥዋ ሲመጡ ይኸው ኑር የሚባለው የግራኝ ባሕር ነጋሽ ከመንገድ አግኝቶ መቀማቱን ይገልጽና እንደዚህ ሲል ያስከትላል ።

ይህ ባሕር ነጋሽ (ኑር) ጌታው ንጉሡ (ግራኝ) የመላው ኢትዮጵያ ጌታ መሆኑን የካህኑ ዮሐንስን (ያዓ. ልብነ ድንግልን) ግዛት በሙሉ ድል አድርጎ የያዘ መሆኑን ገልጾ ፖርቱጋሎቹ ከርሱ ጋር የሰላም ግንኙነት አድርገው ባገሩ በብዛት የሚገኘውን ወርቅ የዝሆን ጥርስ ጥርኝ ፤ ዕጣንና ከርቤ ሌላውንም ሁሉ ባሪያም ጭምር ቢነግዱ እንደሚጠቀሙ በበኩሉም ለስንቅ የሚሆን ማናቸውንም በብዛት እንደሚሰጥ ከዚህ በፊት የማረካቸውን ሐብቶች እንደሚመልስ ስለሞቱትም ስድሳ ሰዎች ካሣ እንደሚከፍል ለመርከቡ ጠቅላይ ሹም (ለእስጢፋኖስ ደጋማ) ፤ ላከ በማለት ያረጋግጥና ቀጥሎ በርሱው ምክር የእስላሞቹን ማታለል በማታለል ለመመለስ የመርከቡ ጠቅላይ ሹም እስጢፋኖስ ደጋማ ይኸንኑ የባሕር ነጋሽን አሳብ በመደገፍ በመዠመሪያ ፩ ቤርሜል የወይን ጠጅ ሰጦታ ልኮ ለስንቅ ስለሚመጡት ከብቶች ዋጋ ሺ ጨርቅ በመላክተኛው እጅ መላኩን ከዚህም ጋር ከዚህ በፊት ስለተላከው ሺ ጨርቅ ግድ የለም እነዚያም የተገደሉት ፷ ሰዎች ከኛ ሽፍ

(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ገጽ 19 ። እዚህ ላይ ባሕር ነጋሹ ይስሐቅ መሆኑን ኢኖ ሊትማን በቍጥር 2 ማስታወሻ ይገልጻሉ ገጽ 84 ።

ተው በገዛ ጥፋታቸው የሞቱ ስለሆነ ባሕር ነጋሽ ስለነርሱ አሟሟት እንዳያ
የቀረውን የንግድ ውል ግን አሁን ያለነው በሰሙነ ሕማማት ላይ ስለሆነ በዚህ ሳ
ንት ምንም እንዳንሠራ ሃይማኖታችን ስለሚከለክለን ሕማማት ከወጣ በኋላ ግ
ቸውንም ባሕር ነጋሹ የሚመኘውን የንግድ ውል እናደርጋለን ብለህ ንገረው ብለ
መላከተኛውን መልሶ እንደ ሰደደው ያመለክታል ።

ከዚህ በኋላ በምሥጢር ሌሊት ማርቲኖ ኮሮአ የሚባለው በዋናው መሪ በእ
ጢፋኖስ ዳጋማ ትእዛዝ ፺፱ የመርከበኛ ጦር ይዞ በሌሊት ሄዶ አርኪቆ ላይ ከነ
ታደሩ ወርዶ ጠላት ሊያመልጥበት የሚችለውን መንገድ ሁሉ በድንገት ከቦ ያዘና
ይዋጋቸው ጀመር ። በዚህም ጊዜ ቀጥራቸው ትንሽ የሆነ ቱርኮችና (ቱርታዐሊሉ-
ዓረቦች) ገድለው ዘረፋዋቸው በዚያን ጊዜ ባሕር ነጋሽ (ኑር) የንጉሡን (ግራኝ ))
መሸሽ ሲያይ (1) እርሱም እየሸሸ አዝማቹ ማርቲኖ ኮሬአ በአለበት በኩል ሳያ
በው ሲመጣ ሰዎች አውቀውት አንዱ የፖርቱጋል ነፍጠኛ ተኩሶ ገደለው ። እር
ሱን ለማዳን (ወይም ለመውሰድ) ብዙ የእግረኛና የፈረሰኛ ወታደሮች እዚያው
ላይ አለቁ ፤ የቀሩትም ሸሹ ። ከዚያ በኋላ በምክር የባሕር ነጋሹ እራስ ተቆርጦ
ጭንቅላቱ ወደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ተልኮ ስለነበር ንግሥቲቱ በዚሁ መደሰታ
ቸውን ከአዝማች ኪሩቤል ትግሬ መኰንን መስማታቸውን ገሥን ቤርሙዴዝ በዝር
ዝር ይጽፋል (2) ።

JSIC

በዚህ ዓይነት የማታለልና የማዘንጋት ውጊያ እስጢፋኖስ ዳጋማ ከውስጥ
አወቁ ከገሥን ቤርሙዴዝ ምክር በመውሰድ ከዚህ በፊት እስላሞቹ አታለው የፈጁ
ዋቸውን የስድሳ ሰዎቹን ደም ተበቀለ ። ከዚህም ጋር ይህ ከምጥዋ ወደ ደቡብ የሚ
ገኘው የአርኪቆ ወደብ ቱርኮች ጭምር የመሸጉበት ወደብ ስለነበረ በዚያ ያለውን
ተከላካይ ጦር አጥፍቶ ወደቡን እንደ ምጥዋ ነፃ አድርጐ በእጁ ካገባ በኋላ እንግ
ዲህ ቀጥሎ ያለው ጉዳይ ጦር መርጦ ለተመረጠው ጦር አዝማች ሾሞ ለንግሥት
ሰብለ ወንጌልና ለዓፄ ገላውዴዎስ መላክና እርሱ ወደመጣበት የእንደራሴነት ስፍ
ራው ወደ ጐአ (ሕንድ) መመለስ ብቻ ነው ።

በግራኝ አህመድ ውስጥ በርከት ያሉ በኑር ስም የሚጠሩ ሹማምንት ስላሉ
ይህ ጭንቅላቱ ተቆርጦ ለንግሥት ሰብለ ወንጌል የተላከው የትኛው ኑር መሆኑን
ለይቶ ማወቁ ይቸግራል ። ታሪከ ነገሥቱ በአንድ ቦታ ላይ የፈረንጆቹን መምጣት
ከተናገረ በኋላ ቀጥሎ ወቀተልዎ ለአባ እስማን ኑር ስለሚል ከዚህ በፊት በብዙ
የጦር ቦታ የዋለውን የንጉሡን የበኩር ልጅ ፊቅጦርን የገደለው አብሳማ ኑር ይሆ
ናል ያሉ አሉ ። ነገር ግን ሙሴ በሴት ሬኔ በመጨረሻ ከግራኝ አርኪቆን የተሾ

(1) ቤርናጋስ ኖሮ (ባሕር ነጋሽ ኑር ማለቱ ነው) እዚህ ላይ የንጉሡን መሸሽ ሲያይ ብሎ የጻ
ፈው በዚህ ጊዜ ግራኝ እራሱ በዚህ ቀበሌ ያለ አይመስልም ። እርሱ ቢኖር ትልቅ ጦርነት በተደ
ረገ እርሱ በዚህ ሰዓት በዚያው በደንቢያ ወይም በትግሬ ግዛት ሳይሆን አይቀርም ።

(2) Histoire de christianisme....... ገጽ 104 - 109

መው ሸሪፍ ኑር ነው ብለዋል (1) ። ነገር ግን ባለፈው ግራኝ ወደቤገምድር ሲሄድ ባደረገው ሹም ሽር ለደሆኖ ወደብ ሸሪፍ ኑርን ሽሮ ሱልጣን ቤን ኢስማኤልን (ያገሩን ተወላጅ) እንደሾመ ተመልክተናል ። ምናልባት በዚህ ባሁኑ ጊዜ ኑር ወደ ቀድሞ ሹመቱ ተመልሶ ይሆናል ።

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ የጻፈው ለንጉሡ በራፖርት እንጂ በመጽሐፍ መልክ አይደለም ። ስለዚህም አጻጻፉ በጣም አጭር ነው ። ለተደረገው ነገር ሁሉ ቀንና ዓመተ ምሕረት ማድረግ አይወድም ። ምናልባት የአጻጻፉን ስጦታ እናውቅም እንጂ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቶት ቢሆን ኖሮ የአርኪቆን ወደብ አወዳደቅ የኑርን አሟሟት ከዚህ ሰፋ ባለ አኳኋን ሊዘረዝርልን በቻለ ነበር ። ነገር ግን ስለዚህ ስለአርኪቆው ጦርነት ሌላ የወሬ ምንጭ እንዳለመኖሩ መጠን ቢኖርም በአጭር ዓረፍተ ነገር የተወሰነ በመሆኑ የዚህኑ የቤርሙዴዝን አጻጻፍ መሠረታዊ አድርገን መቀበል ግዴታ ነው ።

በአጻጻፉ ቀንና ዓመተ ምሕረት ካለመጨመሩ በቀር ከማዕርግ ስምና ከመጠሪያ ስም ላይ ሲደርስ አጣርቶ አይጽፍም ። ከ፰ ዓመት በኋላ አጠገባቸው ተቀምጦ በዚህ ስም አለመጠራታቸውን እያወቀ በክርስትና ስማቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ወይም በስመ መንግሥታቸው ዳዊት ወይም በወታደራዊ ስያሜያቸው ወናግ ሰገድ በማለት ፈንታ ከርሱ በፊት በወሬና [illegible] የተጠሩበትን ካህኑ ዮሐንስ የሚባለውን ስያሜ ሁልጊዜ በጽሑፉ ሲጠቀምበት ይታያል ። ጽሑፉ ከመዠመሪያው ላይ ብቻ አንድ ጊዜ ልብነ ድንግል ለማለት እናዲንገል ብሏቸዋል ። በተረፈ ባሕር ነጋሽ ሲል ባርናጋስ ኑር ለማለት ኖሮ ግራኝ በማለት ፈንታ ጎሮንሀ ብሎት ይገኛል ። የኢትዮጵያ ገገር ወይም እንደ እስላሞቹ አጠራር ይማም አህመድ በማለት ፈንታ ግራኝን የዘይላ ንጉሥ ይለዋል ።

ከዚህም በቀር በጽሑፉ ውስጥ ራሱን ገና ያልጸደቀለትን ሹመትና የሹመት ስም እያወሳ ከሊስቦን ወደጎአ የመጣ ጊዜ እገሌና እገሌ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ አድርገው በሰልፍ አክብረው ተቀበሉኝ ዋናው አዝማች እስጢፋኖስ ደጋማን እንደ ዚህ ብዬው ወይም ይኸን አድርግ ያልኩትን ሁሉ ያደርግ ነበር ፤ እያለ የራሱን መከበሪያ ሰፋ አድርጎ እንደሚጽፍ ይታያል ፤ ነገር ግን የፓትሪያርክነቱን ሹመት የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት እንዳልሾሙት ወደፊት እናነባለን ። በዚህ ምክንያት ሁሉ ከዚያ ወዲህ የተነሣ ጸሐፊ ሁሉ ምንም እንኳን የቤርሙዴዝ ጽሑፍ ሌላ ከማጣት የተነሣ መሠረትነቱን ባይለቅም ከርሱ አተራረክ ወደፊት ለምናነበው ለሚጉኤል ደ. ካስታንሆዞ መጽሐፍ ዋጋ ይሰጣል ።

(1) ዓረብ ፋቂህ የረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 75 ማስታወሻ ቍጥር 1

# ምዕራፍ ፲፱
## የክሪስቶፎሮስ ዳጋማ መሾም

ክሪስቶፎሮስ ደጋማ ወደ ኢትዮጵያ ለሚዘምተው ጦር አዝማች ሆኖ ሕይወቱን የሰዋ ሲሆን የሕይወት ታሪኩ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቀ ሊሆን ይገባ ነበር ። ዳሩ ግን በተለይ የርሱን የሕይወት ታሪክ በተለይም የልደቱና የዕድገቱ ሁኔታ በትክክል የተጻፈ አላጋጠመኝም ።

ይሁን እንጂ ሙሴ አልቤር ካሜረር ከየአለበት አጠራቅመው ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ላይ ክሪስቶፎሮስ ከታላቅ ወንድሙ ከእስጢፋኖስ ደጋማ ጋር ሆኖ ለመዠመሪያ ጊዜ ከሊስቦን መንፈስ ቅዱስ (ESPRITO SANTO) በሚባል መርከብ ተሳፍሮ ወደ ሕንድ ሲመጣ ዕድሜው ፲፮ ዓመት እንደነበረ አረጋግጠዋል ። በዚህ ዓይነት የተወለደው በ፲፭፻፲፮ ዓ. ም. ነው ማለት ነው (1) ።

በኋሁ ደራሲ መጽሐፍ በዚሁ መርከብ ተሳፍረው ወደ ሕንድ በሚጓዙበት ጊዜ ማዕበልና ሞገድ መርከቡን እየገፋና እያንገላታ እስከ ሞዛምቢክ በወሰደው ጊዜ መርከቡ ከጥፋት ሊድን የቻለው በወጣቱ በክሪስቶፎሮስ ብርታት መሆኑ፤ ወንድሙ እስጢፋኖስ መርከቡን እንደያዘ ወደ ሕንድ ደርሶ ከዚያ ወደ ቻይና በተለይ ማላካ በምትባለዋ ደሴት ላይ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ደርሰው ከዚህ በፊት ባንድ እስላም እጅ በጩቤ ተወግቶ የሞተውን የወንድማቸውን የጳውሎስ ደጋማን ደም ለመበቀል በተደረገው ጦርነት መካፈሉ ፤ ወደ አገሩ ወደ ፖርቱጋል ከተመለሰ በኋላ በወጣትነቱ ጊዜ በሌላውና በተለይ በማላካ (የቻይና ደሴት) በአሳየው ዠብዱ የማላካ ካፒቴን ተብሎ የማዕርግ ሹመት ማግኘቱ ተጽፏል ።

ከዚህ በኋላ ባለፈው እንዳነበብነው በ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. የቱርኩ መንግሥት ባለሥልጣን ሶሊማን ፓሻ በመርከብ ወደ ሕንድ ዘምቶ የዲውን ወደብ ከቦ በሚይጠቃበት ሰዓት (፲፭፻፴፰ ዓ. ም.) ካፄ ልብነ ድንግል የጠሩን እርዳታ ለማፋጠን የተላከው ዮሐንስ ቤርሙዴዝና ኢትዮጵያዊው ጸጋ ዘአብ ባሉበት አዛዡ ሮናን፤ በሚመራው መርከብ ውስጥ ተሣፍሮ ወደ ሕንድ ተመልሶ መጣ ።

የዲውን ወደብ ለማዳን በተለይም ሶሊማን ያፈራረሰውን መልሶ ለማቋቋም በተደረገው ተግባር የትጋት ተካፋይነቱን በማሳየት ከ፲፭፻፴፱ እስከ ፲፭፻፵ ዓ.ም. ድረስ በሕንድ ከቆየ በኋላ ወንድሙ እስጢፋኖስ ደጋማ በኖሮንሃ ፈንታ የሕንድን ጠቅላይ ገዥነት ተሾሞ ባለፈው እንዳነበብነው በ፲፭፻፵ ዓ. ም. ከሕንድ የስዌዝን ወደብና በዚያ ያለውን የቱርክን የመርከብ ኃይል ለመደብደብ በተደረገው ዘመቻ በወንድሙ ውስጥ ያንድ ክፍል መርከብ አዛዥ ሆኖ ዘምቶ ከስዌዝ መልስ ሆኖ ምጥዋ በሠፈሩበት ሰዓት ባለፈው እንዳነበብነው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ካፄ ልብነ ድንግል ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ተልኮ የርዳታውን ወታደር ለማግኘት ከጸጋ

(1) La mer rouge - l'Abissinie et l'Arabie ......... ገጽ 141 - 142



ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሕይወቱን የሠዋው ክርስቶፎሮስ ደጋማና ፊርማው ፤ (ከሊስቦን መጻሕፍት ቤት የተገኘ) ሥዕሉ ከዕድሜው የበለጠ አሸምግሎታል ።

ዘአብ ጋር ከሊስቦን ወደ ሕንድ መጥቶ በመካከሉ ጺጋ ዘአብ ስለሞተ ብቻውን በፊት ከኖሮንሃ ጋር እንደነበረ አሁንም አብሮ ከእስጢፋኖስ ደጋማ ጋር ሆኖ ከሕንድ ወደ ምጥዋ አብሮ እየተጓዘ የርዳታውን ጦር ለማፋጠን ደጅ ከመጥናት ላይ መሆኑ የሚታወስ ነው ።

ስለዚህ እስጢፋኖስ ደጋማ የምጥዋንና የአርኪቆን ወደቦች እጅ ካደረገ በኋላ በቀይ ባሕርም ሊዋጋው የደፈረ የቱርክ የመርከብ ኃይል ስለጠፋ ወደግዛቱ ወደ ሕንድ ከመመለሱ በፊት ከምጥዋ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ የውስጥ ግዛት ገብተው የተጠቃውን የክርስቲያን ሕዝብ ከግራኝ አህመድ ወረራ የሚያድኑ ወታደሮችና ሹማምንት መምረጥ ገመረ ። የተመረጡት ደንበኛ ትጥቅ ያላቸው የወታደሮች ቍጥር ፬፻ ነው ። ነገር ግን ከነዚሁ በቀር ከነርሱም ወገን ከኢትዮጵያውንም በኩል የተሰበሰበው ተከታይ ጀሌ አጃቢውና አሽከሩ ብዙ ነው (1) ።

ለዚህ ዘማች ጦር መሪ በመሆን በግራኝ የተጠቃውን ክርስቲያናዊ መንግሥት ለመርዳት ባላቸው የጋለ የቅናት መንፈስ ምክንያት በምርጫው ጊዜ የፖርቱጋሎቹ የጦር ሹማምንት እኔ ልሁን እኔ ልሁን እያሉ ጠቅላይ ገዥውን እየለመኑ መሻማታቸውን ፤ እርሱንም እባክህ ይኸን የመሪነት ሹመት አማልደህ አሰጠን እያሉ ወደዋናው ጠቅላይ አዛዥ ወደ እስጢፋኖስ ደጋማ አማላጅ እንደላኩት በርሙዴዝ በመጽሐፉ ያረጋግጣል ። ይኸን አደጋ ያዘለውን የመሪነት ክብር ለማግኘት ከተሻሙት ሹማምንት መካከል በዚህ ምዕራፍ አጭር የሕይወት ታሪኩን ያነበብነው ወጣቱ ክሪስቶፎሮስ የእስጢፋኖስ ደጋማ ታናሽ ወንድም ይገኛል ። እስጢፋኖስና ክሪስቶፎሮስ የሕንድን የመርከብ መስመር እንደዛሬ የስዌዝ ቦይ ሳይከፈት አስቸጋሪ በነበረበት ጊዜ በደቡብ አሜሪካና በሞዛምቢክ በኩል ለፖርቱጋል የከፈቱት የቫስኮ ደጋማ ልጆች ናቸው ።

ይኸው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ መሪነቱን በኔ ምልጃ እስጢፋኖስ ደጋማ ለታናሽ ወንድሙ ሰጠው ሲል ሚጉኤል ዴ. ካስታንሆዞ ግን ክሪስቶፎሮስ ደጋማ መሪነቱን የተሾመው በቀጥታ ወንድሙን እስጢፋኖስን ለምኖ መሆኑን ያረጋግጣል (2) ። የሚመስለውም የዚህ የመጨረሻው ነው ። ምናልባት እስጢፋኖስ የወንድሙን ልመና ከሰማ በኋላ የቤርሙዴዝን አስተያየት ጠይቆት ቤርሙዴዝም ይሁን በማለት የጠቅላይ ገዥውን አሳብ ደግፎ ይሆናል ። የክሪስቶፎሮስንም የመሪነት ችሎታ ከባዕዱና ከካህኑ ከቤርሙዴዝ ይልቅ የሚያውቀው የወንድም አለቃውና የሚቀርበው እስጢፋኖስ ነው ።

የሆነ ሆኖ የመሪነቱ ሹመት ለክሪስቶፎሮስ ከጸደቀ በኋላ በርሱ ውስጥ ለመዝመት ቆርጠው የተነሡት ሹማምንት ዶን ገአኦ ዴ. ካስትሮ ፤ ዶን ማኑኤል ዴ. ሊማ ፤ ዶን ፓዩ ዴ. ኖሮንሃ ፤ ትሪስታን ዴ.ታይድ ፤ ማኑኤል ዴ. ሱዛ ተደልድለዋል ።

(1) Histoire du Christianisme .........La croze ገጽ 108
(2) Histoire du Christianisme............. ገጽ 109 ። የፖርቱጋሎች ገማንነት ገጽ 19

በዚህ ሁሉ መካከል መቼም ለአንባቢ የሚገርሙ ሁኔታዎች ይታያሉ ።
፩ኛ. ያን ያህል መከራና ስደት የተቀበሉት ዓፄ ልብነ ድንግል ራሳቸው የጠየቁት የርዳታ ጦር ደርሶ የደኅንነቱን ሥራ ለመመልከት ዕድል ሳያገኙ ርዳታው በየካቲት ወር በቀይ ባሕር ሲደርስ እርሳቸው በዚሁ ዓመት ከስድስት ወር በፊት በመስከረም ወር መሞታቸው ፤
፪ኛ. እስጢፋኖስ ደጋማ ከሕንድ መጥቶ በስዌዝ በምጥዋ በአርኪቆ ወዲያና ወዲህ እንደ ልቡ እየተዘዋወረ የአርኪቆን ወደብ በደበደበበት የግራኝን ሹም የኑርን ጭንቅላት አስቆርጦ ወደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በመላክ ዋናውንም የጦር ርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ በሚዘጋጅበት ሰዓት በአውሮፓ ምሥራቅና በመካከለኛው ምሥራቅ በሰሜን አፍሪካ ዓለምን ያንቀጠቀጠው የቱርክ ኃይል የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን ካርበደበደው ከግራኝ አህመድ ጋር በመተባበር የሚመጣውን ርዳታ ሳያሰናክሉ ርዳታው እንደልቡ ምጥዋ ተራግፎ ወደ ደባርዋ ተጉዞ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ለመገናኘት መቻሉ ነው ።

የሆነ ሆኖ አሁን ክሪስቶፎሮስ ደጋማ የርዳታውን ጦር ይዞ ለክርስቲያናዊው መንግሥት ታማኝ ከሆኑት ከነባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ጋር ሆኖ ያደረገውን ጉዞ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመልከት ።

ISIC

## ምዕራፍ ፪፲

## ከምጥዋ እስከ ደባርዋ የፖርቱጋሎቹ ጉዞ (፲፭፻፵፩ ሐምሌ ፲፭ - ፳፭ ቀን)

በፖርቱጋሎቹ በኩል የሹመቱና የዝግጅቱ ጉዳይ አልቆ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅና ትግሬ መኰንኑ "ኪሩቤል ወይም ሮቤል" ወደ ኢትዮጵያ ለሚዘምተው ጦር ለጉዞ አስፈላጊ የሆነውን ከብትና ስንቅ ከአቀረቡ በኋላ ዋናው መሪ እስጢፋኖስ ደጋማ ወንድሙንና ዘማቾቹን አሰናብቶ እርሱ ከነጭፍራው ከአርኪቆ ወደብ ተሣፍሮ ወደ መጣበት ወደ ሕንድ ተመለሰ ። ወደ መርከቡም ከመግባቱ በፊት ቡራኬ ጠይቆኝ ሰጠሁት ሲል ይኸው ቤርሙዴዝ በመጽሐፉ ያረጋግጣል (1) ።

እዚህ ምዕራፍ ላይ በቤርሙዴዝ አጻጻፍ ውስጥ የሌለ በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ አንዳንድ የታሪክ ልዩነት ይታያል ። በካስታንሆዞ መጽሐፍ ውስጥ የሕንድ ዋና አገረ ገዥ ዶን እስጢፋኖስ ምጥዋ ሠፍሮ ሳለ የቄሱ "ገላውዴዎስ" አዛዥ ባሕር ነጋሽ የሚባለው ደብዳቤ ይዞለት እንደመጣ በደብዳቤው ላይ ንጉሡ ግዛቶቹ ፲፬ ዓመት ሙሉ በዓረቦች እንደተያዙና ሕዝቡም የሚበዛው ምርኮኛ መሆኑን አሳስቦ ወንድሙ "የፖርቱጋል ንጉሥ" ጉልበት የሌላቸውን ደካሞች መርዳት ልማዱ ስለሆነ ርዳታ እንዲልክለት እነዚህም የኢትዮጵያ አገሮች በግርማዊነቱ ንጉሥ ስም እንዲታዘዙ ይሆናል የሚል ቃል በደብዳቤው ላይ እንዳለበት እንደራ

(1) Histoire du Christianisme ገጽ 111 ።

ሴውም ቃሉን አንብቦ ከተረዳና ከሹማምንቱ ከተመካከረ በኋላ በወንድሙ አ
ችነት የጠሩን እርዳታ ለኢትዮጵያ ንጉሥ እንደላከ ይገልጻል (1)።

ራሱን ደብዳቤውን ወይም ትክክለኛ ቅጅውን እስከናገኝ ድረስ ይኽን ሰ
መሰለው ታሪካዊ ምዕራፍ ሰፋ ያለ ሐተታ እንደ ልብ መስጠት ከስሕተት ሊ
ሊጥል ይችላል ። ይኽን ደብዳቤ የላከውን የንጉሥ ስም ካስታንሆዞ ስለአልጠ
ሰና አሁን እስጢፋኖስ ዶጋማ ምጥዋ በሰነበተበት ጊዜ ፰ ወራት ግድም ስለአለ
ያሁኑን የጦር ርዳታ ልመና የጻፉት ሠራዊ በነበሩበት ሰዓት ወጣቱ ገላውዴዎ
መሆን አለባቸው ። ይኽንንም የሚያስረዳን ዓፄ ገላውዴዎስ በሸዋ ከነስረዲን ጋር
ከተዋጉ ወዲህ ወደ ትግሬ ሲጓዙ ከፖርቱጋሎቹ ዘንድ በቅድሚያ ሄዶ ተገናኝቶ
የነበረው አሪያስ ዲያስ የሚባለው የፖርቱጋልና የሕንድ ክልስ ፖርቱጋሎች ደብ
ዳቤ አስይዘው የላኩት አብሮ እንደነበረ ታሪክ ነገሥቱ በግዕዝኛ ስለሚጠቅስ ይኽን
የመሰለው መልእክት ካፄ ገላውዴዎስ ዘንድ መላኩን ያመለክታል ። አሪያስ ዲያ
ከዚህ በፊት እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፳ ዓ. ም. ከነሮድሪጎ ደሊማ ጋር ወደ ኢት
ጵያ መጥቶ አገሩን ስለሚያውቅ አሁንም ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ በቅድሚያ መላ
በዚሁ ምክንያት ነው ። ወደፊትም ያፄ ገላውዴዎስ ባለሟል ሆኖ ሃይማኖቱንም
ወደ ተዋሕዶ ለውጦ ማርቆስ እየተባለ መጠራቱን እናነባለን (2)።

አገሮቹ በግርማዊነቱ ውስጥ ይታዘዛሉ ስለሚለው ቃሉ በትክክል እንደዚህ
መጻፉን አናውቅም ። ነገር ግን ይኽን የካስታንሆዞን መጽሐፍ ወደ ጀርመን የተረ
ጐሙት ሊቁ ሊትማን ስለዚሁ ጉዳይ በቍጥር ፩ ሐተታ በመስጠት ይህ ንግግር
የምሥራቅ ሕዝቦች ንግግር ነው ። ማናቸውም የምሥራቅ ሕዝብ እንግዳ ወደቤቱ
ሲጠራ "ቤቱ ያንተ ነው ግባበት" ይላል ብለው አብራርተውታል ። በእርግጥም
ግራኝ ከሞተ በኋላ በዓፄ ገላውዴዎስና በቤርሙዴዝ መካከል የሃይማኖት ጠብ
በሰፊው ተነሥቶ አከራከረ እንጂ በውላቸው መሠረት አገሪቱን በበላይ ልግዛ
ብሎ የፖርቱጋል መንግሥት ምንም ዓይነት ክርክርና ጠብ አላነሣምና የሊትማን
አስተያየት የሚደገፍ ነው ።

የሆነ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ለሚዘምተው ጦር ለመሪነት የተመረጠው ወጣቱ
ክሪስቶፎሮስ ዶጋማ በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ (3) ከዋናው ጠቅላይ አዛዥና ከታ
ላቅ ወንድሙ ከእስጢፋኖሳ ተሰናብቶ በውስጡ ሆነው ይኽንኑ ቅዱስ ዘመቻ ለመካ
ፈል የተመደቡትን ሹማምንትና ፬፻ ወታደሮች አስከትሎ መድፎቹንና ጥይቶቹን
እነባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ባቀረቡለት ግመልና በቅሎ አስጭኖ ከምጥዋ ወደብ ተነ

(1) የፖርቱጋሎች ዝግጅት ገጽ 19 ፣
(2) "አርትዓ ፍኖቶ ንጉሥ ማር ገላውዴዎስ መንገለ ትግራይ ኀበ ኀለዉ ኢማም አህመድ ወዘሎሙ ሠራዊቱ ወምስሌሁ ኅቡረ ማርቆስ አፍርንጋዊ ዘመጽአ ምስለ መጽሐፈ መልእክቶሙ ለአፍርንጅ ዘጸሐፉ ኀቤሁ እንዘ ይኄትዕዎ ከመ ይሚም ጽላሎቶ ውስተ ትእይንቶሙ . . ." ትንዘልማን ያሳተመው የገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ገጽ 20 La mer Rouge A. Kammerer ገጽ 116 ።
(3) እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፵፩ ሰኔ ፱ ቀን እንደ ካስታንሆዞ ፣ እንደ ካሜሬር ፮ ይሆናል ።

ሥቶ የባሕር ነጋሹ ከተማ ወደ ሆነው ወደ ደባርዋ ከተማ ጉዞውን ገሥመረ ።

ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ባለው ዘመን ሁሉ የግራኝን ጦር በመፍራት ክርስቲያናዊው ሕዝብ ለግራኝ መገበርና መስለም የጠላው ሁሉ ቤቱንና እርሻውን እየለቀቀ በየተራራው በየጫካው ይኖር የነበረው ሁሉ የፖርቱጋሎቹን በዚህ ዓይነት ድርጅት ክርስቲያኑን ሕዝብ ለመርዳት መምጣታቸውን የሰማ ሁሉ ከየአለበት እየሰማ በደስታ እየመጣ በክሪስቶፎርስና በባሕር ነጋሹ ዙሪያ ተሰበሰበ ።

ካስታንሆዞ በመጽሐፉ ላይ ቅዳሜ ወደማታ ከምጥዋ ተነሥተው የጨው ውኃ ከሚፈልቅበት ምንጭ አጠገብ መሥፈራቸውን በማግሥቱ እሑድ ከበረሃነቱ የተነሣ መሬቱ ግሎ በሌሊት እንጂ በቀን አላስሄድ ስላለ ውሎ ማድረጋቸውን ከዚያ ወደማታ "ለሰኞ አጥቢያ ማለት ነው" ተጉዘው ጣፋጭ ውኃና ብዙ ቆቅና አውሬዎች ከሞሉበት ወረዳ መሥፈራቸውን ፤ የቀኑ ሐሩር አላስኬድ ብሎ ስድስት ሌሊት መጓዛቸውን አንዳንድ ሥፍራ መድፍና ጥይት ስንቅ የተጫኑትን ግመሎች በቅሎዎች አላስኬድ በማለቱ ጭነቱ እየተራገፈ መድፉን ሳይቀር በብርታት የፖርቱጋሎቹ ወታደሮች እየተሸከሙ በእግራቸው እንደተጓዙ ለዚህ የተቀደሰ ተግባር መልካም አርአያ በመሆን አድካሚውን ጉዞና ሥራ በመካፈል መሪው ክሪስቶፎርስ ደጋግሞ ይጣጣር እንደነበረ ገልጾታል ። የጨው ውኃ ከሚፈልቅበት ወረዳ ደረስን ያለው የምንዙሎ ወረዳ መሆኑ ወደማታ ጣፋጭ ውኃና ቆቅ ከሞላበት ወረዳ ደረስን የሚለውም የሰባርጉማ የደንጎሎ የነፋሲት ቀበሌ መሆኑ ነው ።

ISIC

ከዚሁ አያይዞ ስድስት ቀን ሜዳውንም ተራራውንም በብዙ ድካም አልፈው አንድ የግራኝ ጦር ወደ አፈራረሰው ቤተ ክርስቲያን በጣም ጥሩ አየርና ቀዝቃዛ ውኃ ወደ አለበት ሥፍራ ደርሰው ሁለት ቀን ዕረፍት ማድረጋቸውን ይገልጻል ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ያለበት ሥፍራ ሊቁ ሊትማን እንዳሉት የደብረ ቢዘን ገዳምና ቀበሌ መሆን አለበት ። ከዚያ ፫ ቀን ተጉዘው ወንዝና የካብ ቤት ከሞላበት የአዛዡ ከተማ "የባሕር ነጋሹ ከተማ ደባርዋ" መድረሳቸውን ይገልጻል ።

በደባርዋ ያሉት ካህናትና መነኰሳት መስቀል ይዘው ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው ወደ ክሪስቶፎርስ ደጋግመው መጥተው ግራኝና ጦሩ በአገሪቱና በነርሱ ላይ ያደረሰውን መከራ በዝርዝር በማመልከት እየጮሁ በልቅሶ እየለመኑ እንዲበቀልላቸው በጠየቁት ጊዜ እርሱም "እኔ የመጣሁት እስላሞቹን ለማባረርና እናንተን በየሥፍራችሁ ለመመለስ ስለክርስትና ሃይማኖት ለመሞት ነው" ሲል ሳዘኑት አጽናንቶ አረጋግጦ እንደመለሰላቸው ካስታንሆዞ ያመለክታል ። በዚህ ቀን የክርስቲያኖቹንና የመነኮሳቱን አሳዛኝ ልመናና ጩኸት ሰምቶ ያላለቀሰ ሰው ቢኖር ከሰው ልቆጥረው አልችልም ሲል ይኸው በሥፍራው የነበረው ካስታንሆዞ የተጠቁትን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችንና ለርዳታ ከሕንድ ድረስ የመጡትን የፖርቱጋል ክርስቲያኖችን አስደናቂና ልብ የሚቀሰቅስ ግንኙነት በሰፊው ይገልጻል (1) ።

(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ገጽ 19 - 21

## ምዕራፍ ፻፲፩

## በታሪከ ነገሥት በኩል ያለው የፖርቱጋሎቹ አመጣጥ ።

ያለፉትን ዓመታት የጦርነት ምዕራፎች ያነበበ የነአዝማች አዳሉን የነራስ ወሰን ሰገድን ፤ የነጻሕፌ ላም ሮቤልን የነተሰፋ ልዑልን አሟሟት ፤ የንጉሡን መንከራተት የአብያተ መንግሥቱንና የአብያተ ክርስቲያናቱን ከመነኮሳቱ ጋር መቃጠል የተገነዘበው ሁሉ በአሁኑ ሰዓት የፖርቱጋሎቹ ርዳታ መድረስ በካህናትም በምዕመናኑም ዘንድ የሚቀሰቅሰውን የደስታ ስሜት ለመገመት ቀላል ነው ። ባለፈው ምዕራፍ እንደተገነዘብነው የ፲፭ ዓመቱ ወጣት ክሪስቶፎርስ ከነወታደሩ በረሃውን አውራጃ በብርታትና በጽናት አልፎ የባሕር ነጋሾች ከተማ ወደ ሆነው ወደ ደባርዋ ከተማ የገባ ጊዜ ካህናቱም ምዕመናኑም በሆታ በደስታ ቢቀበሉት አያስደንቅም ። በአቀባበሉም ጊዜ ክርስቲያኖቹ በግራኝ ጦር አጥቂነት ያን ያህል የደረሰባቸውን ግፍና መከራ እያለቀሱ ሲተርኩ የአተራረካቸው ዓይነት ፖርቱጋሎቹንና ደ ካስታንሆዝን ዕንባ አውጥቶ እስከማልቀስ አድርሷቸዋል ማለት ነው ።

የግራኝ አህመድን ሕይወት ከነአገዛዙ አጣድፈው ከኢትዮጵያ ለመሠረዝ በአጭር ታጥቀው ለድል የሚያስተማምን መድፍና ጠበንጃ ይዘው በጋለ የውኃ መንፈስ ከምጥዋ የምንኩሎን የሰሐጢን በረሃ አልፈው በደጋው በደብረ ቢዘንና በዛሬው ISIC አምሐራ በኩል አልፈው ወደ ደባርዋ "ሐማሴን" በደረሱበት በአሁኑ ጊዜ ግራኝ አህመድ ወዴት እንደሚገኝ በትክክል አናውቅም ። የግዕዙ ታሪከ ነገሥት ግማሹ ደረስጌ አንዳንዱም በትግሬ እንደሚገኝ ያወሳል ። እርሱ ቀርቶ አዶሊ ከሞተ ወዲህ የወዚርነት ማዕርግ አግኝቶ ለግራኝ እንደ እንደራሴ የሚቆጠረው ወዚር አባስ "የተስፋ ልዑል ገዳይ" በዚህ በሐማሴንና በሰናፌ ፖርቱጋሎቹ ሥር ሳይሰዱና ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ተገናኝተው ጉራቸውን ከማጽናታቸው በፊት ሊዋጋና የፖርቱጋሎቹን እርምጃ ሊያሰናክል ባለመሞከሩ ሁኔታው በፍርሃት ይሁን ወይም በንቀት አለዚያም ከፖርቱጋሎቹ ጋር እንዳይገናኙ ገላውዴዎስን ባሉበት ገትሮ በመያዝና በማገድ ይሁን አይታወቅም ።

የነዚህ የፖርቱጋሎቹ አመጣጥ በኛ ታሪከ ነገሥት እንደተለመደው በግዕዝ የተጻፈው አጭር ቢሆንም ይኸው አጭሩ አስረጅ ሆኖ ለአንባቢ ታሪካዊ እምነት የሚሰጥ ነው ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ። "ገላውዴዎስ በነገሠ በ፪ኛው ዓመት ቤተ ክርስቲያን በእስላሞች ነገድ ላይ ድልን አገኘች ። ምክንያቱም በዚህ ዓመት ጦርነት እንደ ተኩላ የጠማቸው ውጊያ እንደ አንበሳ የራባቸው የያፌት ልጅ የቶቤል ልጆች ከባሕር ስለመጡ ነው" (1) ።

(1) ወአመ ካልእት ዓመተ መንግሥቱ ለገላውዴዎስ ካዕበ ሞዓት ቤተ ክርስቲያን ላዕለ ነገደ ተገባላት ወምክንያቱሰ ዘሞዓት ቤተ ክርስቶስ አሜሃ እስመ በይእቲ ዓመት ዐርጉ እምባሕር ደቂቀ ቶቤል ወልደ ያፌት ዕደው ኃያላን ወጽኑዓን ፤ እለ ጽሙዓን ለቀትል ከመ ተኩላ ወርኁባን ለቀትል ከመ አንበሳ ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 99 ። ጉንዘልማን ያሳተመው ቃሉን በመለወጥ ገጽ 4-5

እነዚህን ለርዳታ የመጡትን ፖርቱጋሎች ታሪክ ነገሥቱን ያዘጋጀው የያፌት ልጅ የቶቤል "ቱባል" ልጆች የሚልበት ምክንያት በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ከኖህ ልጆች አንዱ ያፌትና ልጁ ቶቤል "ቱባል" ለፈረንጅ ነገድ ሁሉ አባት ነው በማለት ነው (1) ።

በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ከዚህ በፊት እንደአመለከትነው ምንም ባይተካከል አገርና የግል ስም ጨምሮ እንደዚህ ሲል ጠቅሶታል ። "ወበውእቱ ዓመት ወጽኡ አፍርንጅ እለ ተገመስ እምብርትኋል ፤ ወግብጣኖሙ ድንግበቶቡ" ብዙ ጊዜ የምን ጠቅሰው ታሪክ ነገሥት ከመዠመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የተጻፈው ከኢትዮጵያ ሂዶ በሎንዶን ፤ በፓሪስ ፤ በሮማ . . . . . . የሚገኘው አንዳንድ ግልባጭ ሲነበብ በትናንሽ ቃልና ዓረፍተ ነገር እርስ በርሱ ይለያያል ። ዡል ፔሩሾ ፤ ባሴት ሬኔ ፤ ኢኛሲዩ ጉደዲ ፤ አውግስጦስ ዲልማን ወደየቋንቋቸው እየተረጐሙ ግዕዝኛውን በጐኑ አድርገው ሲያሳትሙ ልዩነቱን ሁሉ ለየብቻ የተቻላቸውን ያህል እያበጠሩ ጽፈው አሳትመውታል ።

እላይ የተጻፈው ሙሴ ዡል ፔሩሾ ያሳተሙት ሲሆን ሙሴ ሬኔ ባሴት ያሳተሙት ደግሞ "ወበውእቱ ዓመት መጽኡ አፍርንጅ እለተገመሰ እም ሀገሮሙ ብርትኋል ፤ ወግብጣኖሙ ድንግስቶቡ" ይላል ። ከታሪክ ነገሥቱ አንደኛው "ወጽኡ እምባሕር" ሲል ሌላው "መጽኡ አፍርንጅ" ቢል አንደኛው እምሀገሮሙን ቢጨምር ሌላው ቢያጐድል ዋናው መደምደሚያ አሳቡ "በዚህ ዓመት ካገራቸው ከፖርቱጋል ፈረንጆች መጡ ፤ ሹማቸው ዶን ክሪስቶፎሮስ ነው" ለማለት ነው ። ከዚሁ እያይዞ ወግብጣኖሙ ድንግስቶቡ ካለ በኋላ ". . . . . . ወቀተልዎ ለአባ እስማን ኑር ወከረሙ በድባርዋ (2) ግራኝኒ ከረመ በደረስጌ" ብሎ ፖርቱጋሎቹ በግንቦትና በሰኔ አርኪቆን መትተው ኑርን ከገደሉ በኋላ በሐምሌ ከአርኪቆ ወደ ደባርዋ መጥተው የክረምትን ወራት ባሳለፉበት ወራት ግራኝ ደረስጌ መክረሙን ይገልጻል ።

ከአክሱም ውድቀት ወዲህ ዠምሮ በዚህ በ፲፮ኛው መቶ ዓ. ም. የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ግማሾቹ የቤተ ክህነት ወገኖች የቀሩትም መሃይምንነት ስለሚያጠቃቸው የአውሮፓን ሥልጣኔ በየመልኩ ለመቅሰም እምብዛም እንደማይጥሩ ፤ በዘመኑ ሥልጣኔ ቴክኒክና የእጅ ጥበብ ፍልስፍናም ዕውቀትም ተስፋፍቶ የሚገኘው በአውሮፖች እጅ ሲሆን የፈረንጅን ፊደሉንም ዕውቀቱንም ለማጥናት ወደ ፈረንጅ አገር ሂዶ ግንኙነት ለማድረግ ፖለቲካውንም ለመከታተል ዋጋ ከሚሰጠው የማይሰጠው ክፍል እንደሚበዛ ከዚህ በፊት ያመለከትነው አሁንም በአጻጻፍ ላይ ይታያል ።

የዘመኑ የባለሥልጣኖቻችንና የካህናቱም የመነኮሳቱም የጋለ ምኞት ኢየሩሳሌም ሂዶ የጌታን መቃብር መሳለም ነው ። በዚያም ቢቀመጡ የዚያ አገር (ኢየሩ

(1) ዘፍጥረት ምዕ. 10 ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ምዕ. 1 ቍ. 15
(2) አንዳንዱ የታሪክ ነገሥት ግልባጭ "ወገብሩ ምክራመ" ይላል ትርጉሙ ያው ነው ።

ሳሌም) ነዋሪው ሕዝብ አሁንም እንደ አውሮፓ ያልሰለጠነ ዓረብና ፍልስጥኤም ቱርክ ስለሆነ ፈረንጅም ቢኖር በሃይማኖት ምግባርና ትሩፋት የታሠረ ስለሆነ ኢየሩሳሌም ወይም እስክንድርያ ሄዶ የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ቢኖርም የሃይማኖት ቅርስ ገብይቶ ይመለሳል እንጂ ላገር አስፈላጊ የሆነውን ሥጋዊ ዕውቀት እምብዛም ይዞ አይመለስም ።

የፈረንጅ ዕውቀት የቀሰመ ኢትዮጵያዊ በቤተ መንግሥቱ ካለመኖሩ የተነሣ ቀድሞ እንጣቴዎስ አሁንም ቤርሙዴዝ መላካቸውን ተመልክተናል ። ቤርሙዴዝ ቢዘገይም እርሱን ለመቀስቀስ የተላኩትን አንቷን ፈርናንዴዝና ጋስፓር ሱሪያኖ የሚባሉ ሁለት የአርመን ተወላጆች ናቸው (1) ። ትንሽ የፖርቱጋል ቋንቋ ያውቃል ተብሎ እርሙን ጸጋ ዘአብ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ወደ ሊስቦን ቢላክ የቍራ መላክተኛ ሆኖ መቅረቱን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። አሁንም ወዳገሩ ሳይመለስ በሕንድ ሞቶ ቀርቷል ።

ስለዚህ የዚያን ዘመን ያገራችን ካህኑ ጸሐፊ የአውሮፓውያንን ፊደላቸውን እንደማያውቀው ሁሉ የፈረንጆችን ትክክለኛውን ያገርና የሰው ስም መጨበጥ ስለሚያዳግተው ፖርቱጋል በማለት ፋንታ ብርትጓል አለው ። በዚህም ላይ በግዕዝና በአማርኛ በፐ የሚዠመር ቃል ስለሌለን ፓ የሚለውን በ ብ ለውጦ ብርትጓል ለማለት [illegible]ጁል ። ቀጥሎ ግብጣኖሙ ያለው ብዙ ሐማሴኖች በኤርትራ ከቱርክ ተያይዞ እንደመጣው የኢጣልያኑን ሻምበል ካፒቴን ወይም ካፒታኖ ግብጣን ይሉት እንደነበረው በአገራችን በአማርኛ ሻምበላቸው ወይም እንደፈረንጆቹ ካፒቴናቸው በማለት ፈንታ እንደዘመኑ አነጋገር ግብጣኖሙ ያለው በዚህ ምክንያት ነው ።

ከማዕርግ ስሙ ይልቅ በጣም ተራርቆ የሚገኘው የዚህ የካፒቴኑ መጠሪያ ስሙ ነው ። ግዕዙ "ድንግስቶቡ" ሲለው ከማን አገር ስያሜ ጋር ሊያቀራርበው እንደፈለገ አናውቅም ።

የዚህ የፖርቱጋል መኰንን ትክክለኛ መጠሪያ ስሙ በአገሩ በቀድሞው ፖርቱጋልኛ አጠራር ክሪስቶቫም (CHRISTOVAM) በዛሬው አነጋገር ክሪስቶቫኦ (CHRISTOVAO) ይሉታል (2) ። ትርጓሜው በኛ በአማርኛ የክርስቶስ ወገን በግዕዝኛ "ዘክርስቶስ" ከምንለው ጋር የሚመሳሰል ነው ። ይኸንኑ መጠሪያ ስም ፈረንሳዮቹ (CHRISTOPHE) ግሪኮችና አንዳንድ አገሮች (Christophoros) ሲሉት በየመጽሐፉ ይገኛል ። እኔም የውጭን አገር የመጠሪያን ስም አብዛኛ ጊዜ የግሪክን አጠራር መውሰድ ከጥንት ዠምሮ ባገራችን በግዕዝም በአማርኛም ልማዳችን ስለሆነ ወደፊት እንደሚነበበው ክሪስቶፎሮስ እያልሁ ጽፌያለሁ ።

ከመጠሪያ ስሙ ቀጥሎ የሚጠራበት ደጋማ (De gama) የቤተ ሰብ ስም

(1) Histoire du Christianisme - La Croze ገጽ 101
(2) Historia geral de Etiopia-a-alta cap. vil II-IX-P.B.
Telles viageus de Pedro Da Covilan-Aduerteucia preliminas ገጽ XIV

ነው ። ከመጠሪያ ስሙ በፊት የሚጠራበት "ዶም" እንደፖርቱጋልኛ "ዶን" እንደ እስፓኝ የታላላቅ የቤተ ሰብ አባሎች ፤ የጨዋ ልጆችና የጦር መኰንኖች በመጠሪያ ስማቸው ላይ እየታከለ የሚጠሩበት የአክብሮት ስም ነው ። ዶም ጌታ ወይም ጌታው አለዚያም አቶ አቤቶ ከምንለው ጋር ይመሳሰላል ።

## ምዕራፍ ፻፲፱

## የግራኝ አህመድ ቸልታ - ስለ ደብረ ዳሞ ተራራና ስለ አቡነ አረጋዊ ገዳም የንግሥት ሰብለ ወንጌልና የክርስቶፎሮስ በደባርዋ መገናኘት (፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ሐምሌ)

ቀድሞ ዓፄ ልብነ ድንግልና የጦር አለቆቻቸውን በሽምብራ ኩሬ በአይፈርስ ፤ በዝሆን ዱር እየተዋጋ በሚያሸንፍበት ጊዜ ግራኝ አህመድ ጦርጦራ መሪ ጠርጣሪ ንቁ ተንኰለኛ አጥባቂ ተዋጊ እንደነበረና በርሱ ግንባር ያሉት ንጉሠ ነገሥቱና የጦር አለቆቻቸው ከመዠመሪያው ላይ የደረጀ መንግሥታቸውን በመተማመን እርሱን በመናቅ በቸልታ ብዙ የሚጠበቅ በር ሳያስጠብቁ እየቀሩ ባንድነት ተባብሮ በመግጠም እንደምን እንደተሸነፉ ባላስጠበቁትም በር በሰላይ መሪነት እያለፈ ባይፈር ጨክና በአመራር ዘዴ በማድባትና አደጋ ጥሎ በመውጋት ፈንታ ለየብቻ በመግጠም እንደምን እንደተሸነፉ ባላስጠበቁትም በር በሰላይ መሪነት እያለፈ ባይፈር ስም ሆነ በዋስል ምን ያህል እንዳጠቃቸው በየምዕራፉ የተገነዘብነውን በአሁኑ ISIC ሰዓት እናስታውሳለን ።

አሁን ደግሞ በዚህ ጊዜ ግራኝ አህመድ ከአሥራ አራት ዓመት ዠምሮ ባገሩ ላይ ነግሦ ከያለበት በዘረፋ ወይም በማስገበር ሀብቱ በዝቶ ሚስቶች አበርክቶ የለምለሙን አገር ደምቢያን ለመቀመጫ መርጦ በዚያ ተድላ ደስታውን ከቤተ ሰቡ ጋር ያያል ። በዚህ ምክንያት የውጭ ጦር ሊገባበት የሚችለውን የምጥዋንና የአርኪቆን ወደቦች ከቱርኮች መርከበኞች ጋር በመስማማት በነዋሪ ወታደር በማስጠበቅ ፈንታ እነዚያን ተዋጊ ሹማምንቱን በየለምለሙ አገር ደልድሎ በመሾም ይኸን በረሃማ የምጥዋ ወደብ ችላ ስላለው ለርዳታ የመጡት ፖርቱጋሎች ምንም የታወቀ ተቃዋሚ ሳይኖርባቸው ምጥዋ ገብተው ከምጥዋ ደባርዋ ከዚያም ወደ እምባ ሠነይት አልፈው መሽጎ የተቀመጠውን ጦሩን ሲወጉበት እርሱ በዚያው በደምቢያና በደረስጌ ሆኖ ደስታውን ያጣጥም ነበር ማለት ነው ።

ስለዚህ ደጋግሞ ማሸነፍ ሲገኝ ትምክህትና ኵራት ይከተላል ። ከዚያም ምቾትና ድልወት ተድላና ደስታ ሲበዛ ብልሁና ጠርጣሪው ወደ ቀብራራ ጌታነት ከዚያም ወደ ቸልተኝነት ይለወጣል ማለት ነው ። ወደቦቹን የማስጠበቁ ጉዳይ በቀጥታ ግራኝን የሚመለከት ቢሆንም በተለይ ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በካይሮና በዘቢድ የተሾሙት የዋናው የቱርክ ሱልጣን የሶሌይማን እንደራሴዎች ከግራኝ አሕመድ ጋር ባላቸው የሃይማኖት ዝምድና ያም ቢቀር የወዳጅነት ግንኙነት ችላ ብለው ሳያስቡትና ሳይጠነቀቁ የእስጢፋኖስ ደጋማ መርከብ በድንገት ደርሶ እንደ ልቡ ከምጥዋ ወደ ስዌዝ ትና ጉርብትና ተባብረው ማስጠበቅ የነበረባቸውን

ከስዌዝ ወደምጥዋ ሲመላለስ ማንም አልተዋጋውም ። የእስጢፋኖስ መርከብ በባሕሩ ላይ በድንገት የደረሰ ቢመስልም አርኪቆን ወግቶ ኑርን በመግደል ጠላትነቱን በገሃድ ከገለጸ በኋላ ቀጥሎ የክርስቶፎሮስ ዳጋማ ጦር እንደልቡ ምጥዋ ላይ ተራግፎ የምንኩሎን የስሐጢን በረሃ የደብረ ቢዘንን ወረዳ አልፎ በሰላምና በደስታ ደባርዋ ሲገባ ከእነዚያ ከግራኝ ኃያላን ውስጥ ወሬውን ሰምቶ አንዱም በቶሎ መጥቶ ሊገጥመው አልቻለም ። በዚህ ላይ ከችሎታው ጋር የዘመኑን የጦር መሣሪያ የያዙትን ፈረንጆች መፍራትም እንዳለበት እንረዳለን ።


ደባርዋ ከተማ እንደገቡ ስለ ክርስትና ሃይማኖት የጋለ ቅናት ስለክርስቲያናዊው ሕዝብ ጥቃት የበረታ ቁጭት ያደረበት ክርስቶፎሮስ ዳጋማ በዚሁ በሐምሌ ወር ከዚሁ ከደባርዋ አልፎ ከንጉሡ ከገላውዴዎስና ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ግንኙነት አድርጎ ግራኝን ለመግጠም የሚቻልበትን መንገድ ከባሕር ነጋሽ ይስሐቅና ከሹማምንቱ ጋር ሲመካከር በክረምቱ ምክንያት ወንዞች ሞልተው ስለማያሻግሩ ብርዱም ጠንካራ ስለሆነ ክረምቱ እስኪወጣ ድረስ በዚሁ በከተማችን በደባርዋ ቆይተን በጥቢው በጥቅምት ወር ጉዟችንን እንቀጥላለን ብለው ስለመከሩት ፈቃዳቸውን መቀበል ግዴታ ሆኖበታል ። ከንጉሡ ከዓፄ ገላውዴዎስ ለመገናኘት ላቀረበው ጥያቄ ንጉሡ ከ፪ ወር በፊት ከግራኝ ጋር ተዋግተው ተሸንፈው ተራራማ ወደሆነው አገር ሸሽተው ተቀምጠዋል ብለው እንደነገሩት ካስታንሆዞ በመጽሐፉ ይገልጻል (1) ።

መቼም የወሬ ነገር ሆኖ ነው እንጂ ፖርቱጊዞች ከመምጣታቸው በፊት ገላውዴዎስ በትግሬ ከነገራድ ኡስማን ከነወዚር ሙጃሂድ ጋር እንጂ ከራሱ ከግራኝ ጋር አልገጠሙም ። ከግራኝ ተዋግተው ተሸንፈው ሸሽተዋል ያለው ወደፊት እንደምናነበው በደዋሮ ከነስረዲን ጋር የተዋጉትን ወደ ተራራማ አገር ሸሽተዋል የሚለው ከደዋሮ ወደ ይፋት ከዚያ ደግሞ ወደ ስሜን ሄደው በተራራማው ሥፍራ የተቀመጡትን ይሁን ወይም በስሜን በመጋቢትና በሚያዝያ ወር መካከል የተዋጉትን ይሁን አናውቅም ።

የሆነ ሆኖ ክርስቶፎሮስ የንጉሡን በሩቅ አገር መሆንና በክረምቱ ምክንያት መገናኘት የማይቻል መሆኑን ከአስረዱት በኋላ እንደዚሁ በክረምቱ ወራት ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ባለው ጊዜ ውስጥ ሥራ ፈትቶ መቀመጥ ስላልወደደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ያሉበትን አገር ጠይቆ ከአለበት ከደባርዋ ያንድ ቀን መንገድ በሚወስደው በደብረ ዳሞ ነው ያሉት ባላቸው ከሞቱባቸው ወዲህ ንዛቸውንና ልጆቻቸውን ይዘው በዚህ ተራራ ላይ ተቀምጠዋል ካሉት በኋላ የእርሳቸው መምጣትና በኛና በሕዝባቸው መካከል መገኘት አስፈላጊ ነው ሲል እርሳቸውን ለማምጣት ከፖርቱጋሎች ውስጥ መቶ ወታደር መርጦ ወደ ደብረ ዳሞ ላከ ። ለተላኩት ወታደሮች ዋና መሪ አድርጐ የላካቸው አማኑኤል ደ ኩንሃንና ፍራንቼስኮ ቢልሆንን ነው ።

እነዚህ ፖርቱጋሎች ደብረ ዳሞ ደርሰው ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ወደ ደባ

(1) የፖርቱጋሎች ዝማንነት ምዕ. 2



የደብረ ዳሞ ተራራ ራቅ ብለው ሲያዩት ።

ርኖ ማምጣታቸውን ከመጻፋችን በፊት ትንሽ ስለ ደብረ ዳሞ ገዳም ሁኔታ እንጽፋ ለን ፡፡


ስለ ደብረ ዳሞ ተራራ ብዙ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ከዚህ በፊት በየምክንያቱ ጽፈዋል ፡፡ የካስታንሖዞን መጽሐፍ ወደ ጀርመን የተረጐሙት ሊቁ ሊትማን ከሥራ ጓደኞቻቸው ከንክሬንከር ጋር ደብረ ዳሞን መርምረው ጽፈዋል ፡፡ ራሱ ደ ካስታንሖዞ ስለ ደብረ ዳሞ ደብር ከዚህ ቀጥሎ የሰጠውን ዝርዝር በበኩላቸው ሊቁ ሊትማን አጽድቀውታል ፡፡ ቁመቱ የማይል ሩብ ፤ በተራራው ካለው አምባ ላይ ሁለት ትልልቅ የውሀ ኩሬዎች አሉት . . . . . ከደልዳላው መሬት ላይ የስን ዴና የጤፍ እርሻ ፍየል ዶሮ ንብ ስላለ ይህ ተራራ ብዙ ዘመን ቢከበብም በረሃብና በጥማት ሊወድቅ አይችልም . . . . . . በሰው እጅ የተሠራ ይመስል ሾጠጥ ብሎ የወጣ ማዕዘንማ ስለሆነ በበሩ በኩል ሆነው አሥር ሰዎች ብቻቸውን ቢከላከሉ በቂ ነው . . . . . . ይልና ከዚህ እያይዞ ወደዚህ ተራራ ለመውጣት እላይ ያሉት በፈቃዳ ቸው በጠፍር የሚላክ ቅርጫት ካላኩ በቀር በፍጹም የማይቻል መሆኑንና እንደዚ ሁም ባለፈው ዓመት ግራኝ አህመድ ሌሎቹን ገዳማት የነ አምባ ግሼንን ተራራማ ገዳም ሳይቀር ጥሶ ገብቶ ከበዘበዘ በኋላ ይኸንኑ ገዳም ሰብሮ ሰብሎ ወንጌልን ለመ ግረክ ተራራውን አንድ ዓመት ሙሉ ከቦ ሳይሆንለት ቀርቶ እንደተመለሰ ያረጋ ግጣል ፡፡

ISIC

ይህ ገዳም በአገራችን እንዳሉት እንደ ደብረ ሊባኖስ (የሺምዛናው አባ መጣዕ) እንደ ሰላሌው ደብረ ሊባኖስ እንደ ደብረ ቢዘን በጣም ስመ ጥር ነው ፡፡ ገዳ ሙን የመሠረቱት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አቡነ አረጋዊ (ዘሚካኤል) መሆናቸው በራሳቸው በገድለ አረጋዊ እንደዚህ ሲል ተጽፏል ፡፡ የደብረ ዳሞን ተራራ ለብሕ ትውና ከመረጡት በኋላ ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት ተቸግረው በግርጌው ሆነው ወይኔ ምነው እንደ አሞራ ክንፍ በኖረኝ አለዚያም ምነው ገመድ በኖረኝ እያሉ ሱባዔ ገብተው ሲጸልዩ ሳለ ቅዱስ ሚካኤል ወደ እርሳቸው ቀርቦ « . . . . . አትፍራ ሥልጣን ተሰጥቶሃል ፤ በቀኝ በኩል በዚች ሰዓት ትንሽ እርፈህ ቆይ እግዚ አብሔር በገመድ ፈንታ ትልቅ ዘንዶ ይልክልሃል . . . . » (1) ብሎ እንደተናገራ ቸው ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በሚካኤል አማካይነት ቁመቱ ስድሳ ክንድ የሆነ ዘንዶ ልኮ በዘንዶው ጭራ አቡነ አረጋዊ ተቀምጠው ዘንዶውም እንዳይተናኮላቸው ሚካኤል ሰይፉን መዞ እየጠበቀ ትንሽ ወደ ተራራው መውጣት እንደጀመሩ ዘን ዶው አቡነ አረጋዊን አወንጭፎ እተራራው ጫፍ እንደወረወራቸውና በተራራው ላይ ሲደርሱ ሃሌ ሉያ እያሉ እግዚአብሔርን አመስግነው በዚያ መቀመጣቸውን ይገልጻል ፡፡

መቼም ገድልና ድርሳን ሲጻፍ ይኸን የመሳሰለ የዛሬ አስተዋይ አንባቢ የማ ያምነው የዚያን ዘመንና የዛሬም የዋህ አንባቢ ዕፁብ ድንቅ ብሎ የሚቀበለው ተአ

(1) ኢትፍራህ ተውሕበ ለከ ሥልጣን ወአዕርፍ ንስቲተ ውስተ ዛቲ ሰዓት እንተ ይእቲ መንገለ የማን ወይፈኑ ለከ እግዚአብሔር ተመነ ዓቢየ ሕየንተ ሐብል ፡፡ ገድለ አረጋዊ ተመልከት ፡፡



የደብረ ዳሞን ገዳም ለመጐብኘት ደራሲው በገመድ እየተሳበ ሲወጣ (ፎቶ ጂ. ኤፍ ቶማስ)

ምሪታዊ ታሪክ ስላለ ስለዚህ ጉዳይ ሐተታና ክርክር አያስፈልግም ።

የሆነ ሆኖ አቡነ አረጋዊ ይህን ተራራ ለብሕትውና መርጠው በተቀመጡ በት ዘመን በ፮ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት የአክሱሙ ንጉሥ ዓፄ ገብረ መስቀል ስለ ነበረ ለአቡነ አረጋዊ ሲል የሚያምር ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ሥራው አልቆ ከተመረቀ በኋላም ስመ ጥሩው ባለዜማ ያሬድ መጥቶ ከአቡነ አረጋዊ ጋር ተገናኝተው ከተሳሳሙ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄዶ ፫ ጊዜ ሰግዶ ከተሳለመ በኋላ የሕንፃውን ማማር እየዞረ በአድናቆት ተመልክቶ እንደዚህ እያለ በዜማ መጮሁ በራሱ በገድለ ያሬድ ይገኛል ። «የመለኮት ማደርያ ስለሆንች መላእክት ይመለከቷታል ፤ እኔም የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሕንፃ ውበት እየዞርሁ ተመለከትሁ» (1) ።

የመንግሥት መደብ ከላስታ ወደሸዋ ገዥነት ከዛጉዬ ወገን ከነአኩቶ ለአብ ወደ ይኩኖ አምላክ በዞረበት ዘመን በዚህ በደብረ ዳሞ ገዳም የነበሩት መምህር አባ ዮሐኒ ታላቅ የቤተ ክህነት አባት ናቸው ። ለስመ ጥሩዎቹ አባቶች ለሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ለመምህር ለአባ ኢየሱስ ሞዓ ፤ ለደብረ ሊባኖስ እጨጌ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት አስኬማ (ልብሰ ምንኩስና) ሰጥተው ያመነኮሱ እርሳቸው ናቸው ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመዠመሪያውን አስኬማና ቆብ ቅናት (መታጠቂያ) ከአባ ኢየሱስ ሞዓ ከተቀበሉ በኋላ እንደ ገና ደብረ ዳሞ ሄደው ይኸንኑ የምንኩስና ልብስና ቆብ መታጠቂያውን ከደብረ ዳሞው መምህር ከአባ ዮሐኒ እንደገና ተቀብለው ለአባ ኢየሱስ ሞዓም ይዘውላቸው ከደብረ ዳሞ ወደ ደብረ ሐይቅ (ገዳመ እስጢፋኖስ) መመለሳቸውን የሁለቱ አበው ገድል ይገልጻል (2) ።


ISIC

እንግዲህ ፲፩ ዓመት ሙሉ ከባላቸውና ከልጆቻቸው ጋር ግራኝ ባመጣው የጦርነት መከራ ካገር አገር እየተንከራተቱ በመጨረሻው የባላቸው ሞት ተስፋ ያስቆረጣቸው ንግሥት ሰብለ ወንጌል ግራኝ ሊደርስበት በማይችለው በዚህ ተራራ በተከበረው በአቡነ አረጋዊ ገዳም ተቀምጠው ሳለ እርሳቸውን ለማምጣት እነዚያ ክርስቶፎሮስ የላካቸው ሹማምንት ወታደሮቻቸውን አስከትለው ወደ ተራራው ጥግ ደረሱ ። ከደረሱ በኋላ ከተራራው ግርጌ ለሚገኘው የጠባቂዎች (ዘበኞች) አለቃ ንግሥቲቱን ለመርዳትና ለመውሰድ መምጣታቸውን በነገሩት ጊዜ ሹሙ በቶሎ ለንግሥት ሰብለ ወንጌል መልእክቱን አደረሰ ።

በዚህ ላይ በንግሥቲቱና በቤተ ሰባቸው ዘንድ የሚሰማውን ደስታ ለመገመት ቀላል ነው ። ያልታደሉት ንጉሡ ነገሥት ዓፄ ልብነ ድንግል ያን ያህል ዘመን በግራኝ ወረራ በመከራና በስደት ሲኖሩ ይኸን የደኅንነት ዘመን በደስታ ሳያዩ ብሥ

(1) ይሐውጽዋ መላእክት እለ በሰማያት . . . . . . እስመ ማኅደረ መለኮት ይእቲ አድከዋ እድከዋ ወርኢኩ ስነ ሕንፄሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን . . . . . . የኢ.ት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ምዕ. 58

(2) ገድለ ኢየሱስ ሞዓ መምህር ዘደብረ ሐይቅ Stanislaskur ወደ ፈረንሳዊ ትርጉም Secretariat du Corpusco በ፲፱፻፷፩ ያሳተመው ገጽ 37 ‑ 40



በደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ያለው የአቡነ አረጋዊ ገዳም ራቅ ብለው ሲያዩት (ራሴ ያነሣሁት)።

ISIC

ራቱን እንኳን ሳይሰሙ ከአንድ ዓመት በፊት መሞታቸውን ንግሥት ሰብለ ወን ጌል ሲያስቡት በዚህ ጊዜ እንደሚያሳዝናቸው የታወቀ ነው ። የሆነ ሆኖ በጠቅላላው ለአገራቱና ለሕዝቡ ደኅንነት እነዚህን በእነርሱ እጅ የሌለውን የጦር መሣሪያ የያዙትንና በታላቅ ጉጉት የተጠበቁትን ፖርቱጊዞች ንግሥቲቱ ሲያዩ ያለፈውን ሁሉ ኀዘንና መከራቸውን ያስረሳቸዋል ። የባላቸውንም ኀዘን በዚሁ ይጽናኑበታል ።

ስለዚህ ከላይ ከአምባው ሆነው ወሬውን እንደሰሙ ሁለቱንም የፖርቱጋል ሹማምንት በቅርጫት አስወጥተው በደስታ ተቀብለው ልጆቼ በማለት በፍቅር አነጋግረው ሲጨርሱ በደንገጡሮቻቸውና ባሽከሮቻቸው ታጅበው ከዚህ አምባ ለመዝመሪያ ጊዜ ለመውረድ በመቻላቸው ፈጣሪያቸውን ለቅሶ ጭምር በተደባለቀበት ደስታ እያመሰገኑ ወርደው በተራራው ሥር ካሉት ጋር ተገናኙ ።

ደ ካስታንሖዞ በዚሁ እነ አቶ ዮና ወደ አማርኛ በተረጐሙት መጽሐፍ ላይ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በ፴ ሴቶች በ፶ ወንዶች ታጅበው ከተራራው ወርደው በተ ዘጋጀላቸው በቅሎ ወጥተው ወደ ደባርዋ በአማረ አጀብ ሲጓዙ በቅሎውን ጭምር የሚሸፍን ትልቅ የሐር አጐበር ሰዎች ይዘውላቸው እንደነበረ ፣ ራሳቸው ደግሞ ፊታቸውን በሚያሳይ ዓይነ ርግብ ሸፍነው ከውስጥ ከሕንድ የመጣ ነጭ ልብስ (ቀሚስ) ለብሰው በዚያ ላይ የዓረቦችን ካፖርት የሚመስል የወርቅ ዘርፍ ያለበት በርኖስ ለብሰው እንደነበረ እርሳቸው በጀልባ ሲሄዱ ታማኙ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ የማዕርግ ልብሱን (የአንበሳ ጐፈር) ለብሶ ቀኝ እጁን አውጥቶ የበቅሎውን ልጓም ይዞ እየመራ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ወዳለበት እየተጓዙ እንደደረሱ ይገልጻል ። ክርስቶፎሮስ ደጋማም ጭፍራውን ይዞ ሄዶ ባንድ ቦታ ላይ ተገናኙ ። ከዚህ በኋላ ክርስቶፎሮስ ደጋማ እርሳቸውንና አገራቸውን ከእስላሞቹ ጋር ተዋግቶ ነፃ ለማውጣት በፖርቱጋል ንጉሥ ትእዛዝና በሕንድ አገረ ገዢ ፈቃድ መምጣቱን እርሱና እዚያ በሰልፍ የሚታዩት ፖርቱጊዞች ሁሉ ንግሥቲቱንና ወገኖቻቸውን ወደ ቀድሞው ሥፍራቸው ለመመለስ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ለመዋጋት በሞታቸው የቆረጡ መሆናቸውን ከማስረዳት ጋር ሰፋ ያለ አስደሳች ዲስኩር አደረገላቸው ።

ንግሥት ሰብለ ወንጌልም በሰሙት አነጋገር ተደስተው ኃላፊውን ዶም ክርስቶፎሮስን ካመሰገኑ በኋላ ወንድማቸው የፖርቱጋል ንጉሥ ይኸን እርዳታ በመላኩ ከእግዚአብሔር በቀር ብድሩን ሊመልስለት የሚችል እንደሌለ . . . . . አረጋጣው ዋናውን አገረ ገዥ (እስጢፋኖስ ደጋማ) ለእርሳቸውና ለልጃቸው (ለገላውዴዎስ) ስለሠራው ውለታ እነዚህ አገሮች የርሱ በመሆናቸውና በርሱ አገሮች ዓይነት በመተዳደራቸው ለፖርቱጋል ንጉሥ ውለታው ይመለስለታል የሚል መልስ መስጠታቸው በዚሁ መጽሐፍ ላይ ተገልጿል ። (1) ።

እስላሞች የወሰዱብን አገር ነፃ በወጣ ጊዜ እነዚህ አገሮች የርሱ ስለሚሆኑ

(1) የፖርቱጋሎቹ ዠማንነት ምዕራፍ 4 - 5

የፖርቱጋል ንጉሥ ውለታው ይመለስለታል የሚል አነጋገር ከንግሥቲቱ አንደበት በዚያን ሰዓት ቢወጣ አያስደንቅም ። ይኸን ዲስኩር የተለዋወጡበት ሥፍራ በደባርዋና በደብረ ዳሞ መካከል ስለሆነ እነዚህ አገሮች የሚሉት የምጥዋ ወደብ ነክ የሆነውን አውራጃ እንጂ መላዋን ኢትዮጵያን አይመስልም ። ከባለቤታቸው ጋር በነበሩበት በሰላሙ ጊዜ እነ ሮድሪጎ ከፖርቱጋል ንጉሥ ተልከው ከ፲፭ ዓመት በፊት መጥተው በተመለሱ ጊዜ (እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፳ - ፲፭፻፳፮ ዓ. ም.) በዘይላና በምጥዋ ወደብ የፖርቱጋል ወታደር ከኢትዮጵያ መንግሥት ስንቅ እየተቀበለ ከግብጾቹም ሆነ ከቱርኮቹ እየተከላከለ እንዲቀመጥበት ፍራንቼስኮ አልቫሬጽም የዚሁ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ሕዝቡን ከአረመኔነትና ከእስላምነት ወደ ክርስትና እንዲያመጣ በደብዳቤ መፍቀዳቸውን በአሁኑ ሰዓት ማስታወስ አለብን ። ስለ ዚህ የፊተኛውም የደብዳቤ መንፈስ የአሁኑም የንግሥቲቱ አነጋገር ከፊተኛው ተስፋ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ። ይኸንንም ለማለት የሚያስችለን ከመሀመሪያ ከዓፄ ልብነ ድንግል ዠምሮ ሊቆጣጠሩት ላልቻሉትና ቱርክ ለያዘው የባሕር ዳር አውራጃ ከቱርክ ከእስላሙ እጅ አስወጥተው በክርስቲያን መንግሥት እጅ ለማስገባትና በዚሁ ሰላም ለማግኘት ያለውን የቤተ መንግሥቱን ነዋሪ ምኞት በመደገፍ ነው እንጂ ያገርን ክብርና ነፃነት ባዕውርነት በመደገፍ ታሪኩን አቃውሶ አያደርጉትም ለማለት አይደለም ። በዚያ በጭንቅ ሰዓትም ከወደቡ ሌላ እነዚህንም የደባርዋንና የደብረ ዳሞን አካባቢ በፖርቱጋል ንጉሥ ሥልጣን ውስጥ እንዲሆኑ ፈቅደው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ በሚቀጥለው ዘመን እስከ ዓፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት (፲፭፻፳፩ - ፲፭፻፶፯ ዓ. ም.) ድረስ ይኸን የምጥዋና የአርኪቆ ወደቦች ይነስ ይብዛም የአውራጃው ቀበሌ ከቱርክና ከግብጾች ሥልጣን ሳይወጣ መቆየቱ ቱርክም ሲወጣ ኢጣልያ ተተክቶ የሆነውን ሁሉ እንባቢ ስለሚያውቀው አሁን የዚህን ጉዳይ ትተን ወደዋናው ታሪክ እንመለስ ።

በበኩሉ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ርዳታውን ይዞ በመጣበት ጊዜ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስነት ተሾሜአለሁ የሚለው ስለንግሥት ሰብለ ወንጌል አመጣጥና አቀባበል ታሪኩን ካስታንሆዞ ከተረከው ለየት አድርጎ እንደዚህ ሲል ያመጣዋል ። «ንግሥቲቱ በቶሎ እንድትመጣ ላክሁባት ። በመጣች ጊዜ ሁላችንም በሰልፍና በሥርዓት ሆነን ጥሩምባ እየተነፋ ከከተማው ወጣ ብለን ስለተቀበልናት ይኸን የመሰለውን ሰልፍ ስለአልለመደችው ተገረመች ። ሃይማኖት ነክ የሆነውን ነገር ማክበር ስለምትወድ የኔን ቡራኬና በረከት ጠይቃ ተቀበለች ። ከዚያ ዶን ክርስቶፎሮስን በክብር ተቀብላው ሊረዳት የመጣ በመሆኑ አመሰገነችው ።

ከዚያ በኋላ ወደ ከተማው (ደባርዋ) ተመልሰን ገብተን በማግስቱ ቅዳሴና ክብረ በዓል ተደረገ ። በበዓሉ ላይ ንግሥቲቱ ክሁለት ቆንጆዎች እህቶቿና ካንዲት ልዕልት ልጅዋ ጋር ትራመድ ነበር ። በጸሎት ጊዜ እግዚአብሔር በጠላቶቻ

ችን ላይ ድልን እንዲሰጠን እያለቀስን ለመንነው» (፩) ።

የካስታንሆዞና የዮሐንስ ቤርሙዴዝ አጻጻፍ መሠረቱ አንድ ሲሆን በዝርዝር የሚለያዩበት ምክንያት ካስታንሆዞ የክርስቶፎሮስ ጭፍራና የጦር መኰንን ሲሆን ቤርሙዴዝ ቀድሞ ጠጉር ላጭ እንደ ግማሾቹም ሐኪም የነበረው በመጨረሻ መምህር(MESTRE)እየተባለ ከኢትዮጵያ ሄዶ እርዳታውን ይዞ ከመጣ ጀምሮ በኢትዮጵያ ንጉሥና በሮም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፈቃድ የኢትዮጵያ ጳጳስ እሆናለሁ ብሎ በአሁኑ ሰዓት የቤተ ክህነት ወገን ስለሆነ አተራረኩ መንፈሳዊውን ወገን በመጨማመር ነው ።

ስለዚህ ካስታንሆዞ ወታደር እንደመሆኑ መጠን የአለቃውን የክርስቶፎሮስን ክብሩን ፣ ጀግንነቱን እያገነነ ሲጽፍ ቤርሙዴዝ ደግሞ እንዳይበለጥ እንድትመጣ ላከሁባት ወይም እንደመጣች ከክርስቶፎሮስ ሳትገናኝ ከኔ ቡራኬ ተቀበለች በማለት የራሱን ክብር ይጠብቃል ። ነገር ግን ዞሮ ዞሮ የሁሉም አተራረክ ሲታረቅ የሚችል ዋናው አዛዥ ዶም ክርስቶፎሮስ ንግሥቲቱን ለማስመጣት እነዚያን ሁለት የጦር መኰንኖች የላከ ጊዜ ከንግሥቲቱ ጋር የብዙ ዘመን ዕውቂያ ስላለው በኔም ስም ንገሯት ብሎ በተደራቢ ልኮ ይሆናል ።

በተገናኙም ጊዜ ንግሥቲቱ ቀድሞ የሚያውቁት ቤርሙዴዝ የጵጵስና ቆብ ደፍቶ መስቀል ይዞ ሲያዩት ከልብ ቢሆንም ባይሆንም በቅድሚያ እንደደንቡ ከርሱ ተሳልመው ቡራኬ ተቀብለው ይ1516 ። ከልብ ቢሆንም ባይሆንም ከማለት ያደረስን የኢትዮጵያ የመንግሥቱ የሕዝቡና የንጉሣዊው ቤተሰብ ሃይማኖት እርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሲሆን ከሥር ከዲዮስቆሮስ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበለውን የካቶሊክ ሃይማኖት የያዘውን ቤርሙዴዝን እንደ ጳጳስ መቀበሉም ከርሱም እጅ መስቀል መሳለሙ ቡራኬም መቀበሉ ቅር እንደሚያሰኛቸው በማመን ነው ። ነገር ግን ችግር መርፌ ያስውጣል እንደሚባለው በአሁኑ ሰዓት ነገሩ እንዳይበላሽ ተሳልመው በኋላ ግራኝ ከሞተ በኋላ ያንተን ጵጵስና አልቀበልም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ አትለይም በማለት የተነሣውን ጠብ በሥፍራው ስንደርስ እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፻፲፫

## የንግሥት ሰብለ ወንጌልና የፖርቱጋሎች ጉዞ — ያዬ ገላውዴዎስ ደብዳቤና የቅዱስ ፊቅጦር ትንቢት

ከመጀመሪያ የዓፄ በዕደ ማርያም ባለቤት ንግሥት እሌኒ ማቴዎስን ልከው የወጠኑት ዝምድና በመጀመሪያ እንግዶቹ በመጡ ጊዜ ደጅ በማስጠናታቸውና ችላ በማለት የወቀሰናቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ገጸ በረከትና ደብዳቤ ለዮሐንስ ፫ኛና ለሮማ

(1) Histoire du Christianisme .... ገጽ 112 - 113

ሊቀ ጳጳስ በአልቫሬጽና በአባ ጸጋ ዘአብ አማካይነት የላኩትና ዝምድናውን አጥ ብቀው ያሳሰቡት የቃል ኪዳን ግደኝነት ምንም ቢዘገይ በዚህ ጊዜ እንሆ ፍሬውን አፈራ ። አልቫሬጽና አባ ጸጋ ዘአብ ከኢትዮጵያ ወደ ሊስቦን በ፲፭፻፲፰ (፲፭፻፳፮) ዓ. ም. የሄዱ ጊዜ ጦርነቱ ገና ስላልተነሣ በዚህም ላይ የአባ ጸጋ ዘአብ ቸልታ ተጨ ማምሮ ዘገየ እንጂ አልቫሬጽና ጸጋ ዘአብ የቤርሙዴዝን ያህል በጉዳዩ ተግተው በት ቢሆን ኖሮ ርዳታው ቀደም ብሎ ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን ሊደርስ በቻለ ነበር ። ነገር ግን ቤርሙዴዝ የወረራውን መከራ ባይኑ ያየውን ያህል እነዚያ ለማ የት ስላልቻሉ በዚያ ግንኙነት ችግር በሆነበትም ዘመን የግራኝን ወረራ ወሬው ንም መስማቱ ያዳግታልና ፈጽሞ በነርሱ መፍረድም ችግር ነው ።

ግራኝ አህመድ በኢትዮጵያ ያደረገውን ሁሉ ፤ የሰዉን ማለቅ ፤ የአብያተ ክር ስቲያናቱንና የገዳማቱን መቃጠል ፤ በሰይፍ በትር እየተገደደ የሕዝቡን በጅምላ መስለም ፤ የተመለከተው አገሪቱም ነፃ ስትወጣ ጳጳስ እሆናለሁ ብሎ የሚመኘው ቤርሙዴዝ በ፲፭፻፴፭ (፲፭፻፵፫) ዓ. ም. ርዳታውን አፋጥኖ ለማምጣት በችኮላ ከሄደ ወዲህ በበሽታ ወድቆ አንድ ዓመት በሊስቦን ባይቆይ ኖሮ በሕንድ ደግሞ ነገ ሩን በዝርዝር የሚያውቀው የፊተኛው እንደራሴ ዶም ጋርሲያ ባይሞትና ተከታዩ እስጢፋኖስ ዱጋማ በየምክንያቱ ችላ ባይል ኖሮ ይህ የጦር ርዳታ ራሳቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ከመሞታቸው በፊት ደርሶ ይኸን ያህል ዘመን ከእጇ የሚያድንህ የለም እያለ እየፎከረ ካገር ወዳገር እያሳደደ ያጠቃቸውን የጠላታቸውን የግራኝ አህመድን ውድቀት ራሳቸው ሊመለከቱና በዚህ ረዥም ዘመን ኀዘንና የጦር ፍዳ ያቆራመተውን መንፈሳቸውን ሊያስደስቱበት ይችሉ ነበር ።

ዳሩ ግን ማናቸውም ነገር ያለ ጊዜው አይፈጸምም ። ከሁሉ የበለጠ ንግሥት እሌኒና እርሳቸው የደከሙበት ርዳታ ለልጃቸውና ለአልጋ ወራሻቸው ላዔ ገላው ዴዎስ ማናቸውንም መከራ በትዕግሥት ለተካፈሉት ለባቤታቸው ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል ደርሶ እነሆ በጋለ ፍቅር ከንግሥቲቱና ከገላውዴዎስ ጋር በኅብረት በመ ዋጋት የግራኝን ወራሪነት ብቻ ሳይሆን ራሱን የሕዝበ ክርስቲያኑ ጠላት የሆነውን ግራኝ አህመድን ሲያጠፉ እንመለከታለን ።

ለነገሩማ ምን ንጉሡ ብቻ ፤ በባሌ በዠግንነት የወደቀው አዝማች እዳሉ ፤ በሽ ምብራ ኩሬ በአይፈርስ ላገራቸው ሕይወታቸውን የሰዉት እነ ጸሐፊ ላም ሮቤል ፤ እነ ራስ እስላም ሰገድ ፤ እነ አዝማች ተክለ ኢየሱስ ፤ እነራስ ወሰን ሰገድ ፤ በሠራዬ አዶሌን ከገደለ በኋላ በአባስ እጅ የሞተው ተሰፋ ልዑል ይኸን አስደሳች ጊዜ በዓይ ናቸው ለማየት አልታደሉም ። ነገር ግን አገራቸውን ንጉሣቸውን ሳይከዱ መከራ ውን ፤ ስደቱን በትዕግሥት የተሸከሙት ጓደኞቻቸው ምናልባትም ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው በሕይወት ያሉት ይኸን የደስታ ጊዜ ሲያዩ ከዳተኞቹ እነአናንያ እነ አዝማች ሐይቢ ምናልባት በሕይወት እንዳሉ ይህ የኢትዮጵያ የትንሣኤ ጊዜ ለነ ርሱ የሽብር ጊዜ ይሆንባቸዋል ። የዚህ ጊዜ ሁኔታ በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ጃንሆይ የእንግ ሊዞችን ርዳታ ይዘው ከሎንዶን ወደ አዲስ አበባ የተመለሱ ጊዜ አገሩን ባገለገለ አርበኛና ስደተኛ እንደዚሁም አገሩን ከድቶ ጠላትን ባገለገለው የባንዳ ሹማም

ንት ዘንድ ከደረሰው ጋር ይመሳሰላል ።

የዚህን ባለፈው በካስታንሆዞና በቤርሙዴዝ መጻሕፍት ላይ በዝርዝር ያነበብነውን የፖርቱጋሎች አመጣጥና የዝግንነት ውጊያ ያገራችን ታሪክ ነገሥት እንደተለመደ የሚገልጠው አሥር መስመር በማይሞላ ዓረፍተ ነገር መሆኑን ባለፈው ተመልክተናል ። ስለዚህ ለፊተኛው ጦርነት የዓረብ ፋቂህ ጦርነት እንደጠቀመ አሁንም ካስታንሆዞ መጥቶ በውጊያው አገሪቱን ከመርዳቱ በላይ ይኸን የመሰለ የታሪክ መሠረት በማቆየቱ እናቶ ዮናም ወደ አማርኛ በመተርጐማቸው ፤ ቤርሙዴዝም በበኩሉ ርዳታውን ከማምጣት ጋር ይኸን የታሪክ ቅርስ ስለተወልን እያመሰገንን አሁን ከደባርዋ ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ክርስቶፎሮስ ደጋማ ወደ አምባ ሠነይት ያደረጉትን ጉዞና በዚያ ላይ የተደረገውን ጦርነት እንመልከት ።

በደባርዋ አንድ ወር እንደቆዩ ከዓፄ ገላውዴዎስ የተጻፈ ደብዳቤ ለንግሥት ሰብለ ወንጌልና ለክርስቶፎሮስ መድረሱን ደብዳቤውም (ለክርስቶፎሮስ የተጻፈው) ወንድሙ የፖርቱጋል ንጉሥ ይኸን ርዳታ ስለላከለት መደነቁን ...... መንግሥቱ ሳይጠፋ ክርስቲያን በሆኑ ነጮች አገሪቱ እንደምትድን ከብዙ ጊዜ ዠምሮ ትንቢት እንደነበረና ይህ የተመኘው ርዳታ በዘመኑ በመድረሱ እግዚአብሔር ትልቅ ምሕረት እንዳደረገለት እርሱም ወደ ክርስቶፎሮስ ለመምጣት ማሰቡንና ክርስቶፎሮስም ወደርሱ እንዲሄድ መለመኑን ሁለቱ ያሉበት አገር የተራራቀ መሆኑን ይገልጻል (1) ።

ISIC

ከዚህ በፊት እንዳነበብነው ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤል በ፲፭፻፲፰ (፲፭፻፳፮) ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ በቅዱስ ፊቅጦር ገድል አንድ የፈረንጅ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገናኛሉ ሰላምታም ይሰጣጣሉ የሚል ትንቢት ስለ አለ ይህ ትንቢት በዘመኔ ይፈጸማል ብዬ ተስፋ ሳላደርግ ፈቃዱ ሆኖ ስለፈጸመው የእግዚአብሔር ቅዱስ ስሙ ይመስገን ያሉትን በአሁኑ ሰዓት እናስታውሳለን ።

አሁንም ልጃቸው ገላውዴዎስ ለክርስቶፎሮስ ደጋማ በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ ጠቅሰውት ያነበብነው ይኸው የቅዱስ ፊቅጦር ትንቢት ነው ። ሙሴ ኢኖ ሊትማን የካስታንሆዞን መጽሐፍ ወደ ጀርመንኛ ተርጉመው ባሳተሙት በዚሁ ምዕራፍ ላይ ስለ ትንቢቱ በቍጥር ፳፩ ላይ ማብራሪያ ሲሰጡ የዚህን ዓይነት ትንቢት የተናገረው አንድ የዓረብ አለቃ ነው ይባላል ያሉት ትክክለኛ አይመስለኝም ። አለመሆኑን በመጠራጠር ሊቁ ይባላል የሚባለውን አወላዋይ ቃል መጨመራቸው የተገባ ነው ። የዓረቡንም አለቃ ስሙንና የተናገረበትንም ወቅትና ምክንያት ስለአልጠቀሱ ልናመዛዝነው አልቻልንም (2) ።

ፊቅጦር በፈረንጆች ቪክቶር (ትርጓሜው ድል አድራጊ) የሚባለውን የኛ ከዓ

(1) የፖርቱጋል ዝግንነት ምዕራፍ 6 ፤

(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ገጽ 28 - 29 89

ረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመው ገድሉ «ወሰመየቶ ስሞ ፊቅጦር ፥ ወፊቅጦር ብሂል ትርጓሜሁ አሰሰለ ኀዘንየ ብሂል» ስለሚል የፊቅጦርን ትርጓሜ ኀዘኔን አስ ወገደ ብሎታል (1) ። ኀዘኔን አስወገደ ያለችበት ምክንያት እንደ ገድሉ አነጋገር እናቱ ማርታ ከባሏ ከሆርማኖስ ጋር በአንጾኪያ ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም ነበርና በተለይ እናቱ በዚህ እዝና ስትጸልይ በጸሎቷ ምክንያት ተወልዶ ከኀዘኗ ያረፈች ውን ለማመልከት ነው ።

ይኸው ፊቅጦር በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (፪፻፹፬ - ፫፻፭ ዓ. ም. እንደ አው. ቆ.) ከታላቅ ቤተሰብ ተወልዶ የሮማውያንን አማልክት በሚያመልኩ ቤተሰብ መካከል አድጎ ሳለ እርሱ ግን ክርስትና ተቀብሎ ለአማልክቱ አልሰግድም ብሎ ከአንጾኪያ ወደ ግብፅ መጥቶ በዚሁ በክርስትና ሃይማኖቱ ምክንያት በሰይፍ ተገድሎ በሚያዝያ ፳፯ ቀን በሰማዕትነት የሞተ መሆኑን ገድሉ ያመለክታል ። በዚሁ ምክንያት ይህ ሰው በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደነ ቅዱስ ቴዎድሮስ እንደነ ቅዱስ መርቆሬዎስ የተከበረ ቅዱስ ሰማዕት ነው ። ገድሉ በዚሁ በ፲፫ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝኛ ከተተረጐመና ከታ ወቀ ወዲህ ገድሉም ሰማዕቱም በኢትዮጵያ የተወደደና የተከበረ ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ሌሎቹን ልጆቻቸውን ሚናስን ገላውዴዎስን በጎደኞቹ ሰማዕታት በገላውዴዎስና በሚናስ ሲሰይሙ የመዠመሪያውን ልጃቸውን ፊቅጦ ርን በዚህ ሰማዕት ስም እንደሰየሙት አይጠረጠርም ።

በዚህ ሰማዕት ገድል ውስጥ እንደዚህ የሚል ይገኛል ፤ «በልጅዋ አሟሟት ያዘነችው ማርታ ሌሊት ተኝታ ሳለ ልጅዋ ፊቅጦር በራዕይ ታይቶ እንደዚህ አላት ፤ በግብፅ ወደፊት እስላሞች ድል አድርገው ስለሚገቡ ያፈራርሱታልና በወ ርቅና በብር ያጌጠ ቤተ ክርስቲያን አታሠሪ ፤ ነገር ግን ብዙ ዘመን እንዲቆይ በእን ጨት በደንጊያና በብረት አሠሪ . . . . . ከእስላሞች ግዛት በኋላ በኢትዮጵያ አንድ ቅዱስና የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ንጉሥ ይነሣል ። እርሱም ወደ ግብፅ ይመጣና የእስላሞቹንና የአረማውያኑን ሥራ ያፈራርሰዋል . . . . . በቍስጥንጥንያም (ሮም) አንድ ትውልደ አንበሳ የሚባል ንጉሥ ይነሣና ወደ ግብፅ መጥቶ ከኢትዮጵያዊው ንጉሥ ጋር ይገናኛሉ (2) ከነርሱ ጋር አብረው ያሉት የእስክንድርያውና የቁስጥን ጥንያ ሊቃነ ጳጳሳት ሃይማኖት የኔ ትሻላለች በመባባል ይከራከሩና ሁለቱ ለየብቻ ሲቀድሱ በእስክንድርያው ቅዳሴ ላይ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ ተመስሎ ወርዶ እውነተኛነቱን መሰከረ . . . . . ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያው ንጉሥና የሮሙ (የቍስ ጥንጥንያው) ንጉሥ ሰላምታ ተሰጣጥተው በፍቅር ተለያይተው ወደየአገራቸው ተመለሱ . . . . . . » (3) ።

(1) ገድለ ፊቅጦር ፔሬይራ Pereira በ Corpusco አማካይነት 1962 ያሳተመው ገጽ 229 ።

(2) ቍስጥንጥንያ አንዳንድ ጊዜ ሮም ይባላል ። ይኸውም ከኢጣልያው ሮማ ለመለየት ነው ። ይኸም ከተማ ዛሬ ስጣንቡል የሚባለው የቱርክ ከተማ ነው ።

(3) ገድለ ፊቅጦር ገጽ 243 - 245

ዓፄ ልብነ ድንግልና ዓፄ ገላውዴዎስ በየደብዳቤያቸው የጠቀሱት የትንቢት ጽሑፍ ይህ ነው ። ስለትንቢቱ መፈጸምና አለመፈጸም ብዙ አከራካሪ ነገር አለበት ። ሬቅጦር የነበረበት የዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ፫ኛው መቶ ዓ. ም. መጨረሻ ወይም ፬ኛው መቶ ዓ. ም. መዠመሪያ ሲሆን ግብፅ እስከ ፯ኛው መቶ ዓ. ም. ድረስ የክርስ ቲያን አገር ሆና ሲኖር በ፮፻፴፩ ዓ. ም. በካሊፍ ኡመር ጦር ሠራዊት ከተወረረ ወዲህ አብዛኛው የግብፅ ሕዝብ ዛሬ እንደምናየው እስላም ሆኗል ። ከዓረቦች አገ ዛዝ ወዲህ ግብፆቹ በማመሉክ ሱልጣኖች ሲተዳደሩ ኖረው ባለፈው እንዳነበብ ነው የቱርኩ ሱልጣን ሰሊም የግብጹን ማመሉካዊ ሱልጣን አሊጋውሪን ካሸነፈ ወዲህ ከ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ መዠመሪያው የዓለም ጦርነት (፲፱፻፲፬ ዓ.ም) ድረስ የቱርክ ተገዥ በሆነበት ዘመን ሁሉ የኢትዮጵያ ንጉሥና የሮም ነገሥታት በግብፅም በሌላም ቦታ ተገናኝተው አያውቁም ።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፊት በ፯ኛው መቶ ዓመት ከክርስትና በፊት ግብፅን ድል አድርጎ ከወረረው ከኑብያው (ኢትዮጵያዊ) ንጉሥ ከፒያንኪና ከተከታዮቹ ወዲህ በተለይ በክርስትና ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ የግብፅን መሬት ረግጦ አያው ቅም ። ትንቢት ተፈጸመ ለማለት ያህል የፖርቱጋሎችና የኢትዮጵያውያን ተባ ብሮ የግራኝን ግዛት መጣል ። ወይም የመዠመሪያው የዓለም ጦርነት አሸናፊዎች እንግሊዝና ፈረንሳዊ በግብፅ ገብተው በሚያዙበት ኤኮኖሚውን በሚመሩበት ሰዓት ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ጉርብትና በራቸውን ለማሰብና ከዚህ ትንቢት ጋር ለማገናዘብ የፈለገ ቢኖር አንባቢ ሁሉ የራሱ ነፃነት አለው ።

## ምዕራፍ ፻፲፬

## ክርስቶፎሮስ ዳጋማ በአምባ ሠነይት ከግራኝ ጦር ጋር ተዋግቶ እንደ አሸነፈ (፲፭፻፴፬ ዓ. ምሕረት የካቲት ወር)

ዓፄ ገላውዴዎስ ባለፈው ያነበብነውን ደብዳቤ ለክርስቶፎሮስ ዳጋማ የላኩት በዶ ፋት የግራኝ አህመድን ልጅ አሸንፈው በሸዋ የድል ሙራ ለሕዝባቸው በአሳዩበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ። ደብዳቤውን የያዘው መልክተኛም ከዶፋት የደንክ ልን በረሃ አቋርጦ በአጋሜና በሰራዬ በኩል አልፎ ደባርዋ ደርሶ ይሆናል ። ታሪክ ነገሥቱ ፈረንጆቹን "በደባርዋ ከረሙ" ካለ በኋላ «ግራኝ በደረሰጌ ከረመ . . . . . ከዚያ በታኅሣሥ ወር ተነሥቶ ወደ ትግሬ ሄደ ። ፈረንጆቹም ደባርዋን ለቀው ሄዱ ። ከነርሱም ጋር እቴጌ ሰብለ ወንጌል እነርሱን በምክርና በጥበብ እያጸናች ምግብ እየ መገበቻቸው ገንዘብም እየሰጠቻቸው አብራ ነበረች . . . . . . .» (1) ። ስለሚል

(1) ግራኝኒ ከረመ በደረስጌ . . . . . ወተንሥአ በወርኃ ታኅሣሥ ወሖረ ምድረ ትግሬ እፍርንጅኒ ወጽኡ እምድባርዋ እንዘ ምስሌሆሙ ይቲ (እቴጌ)' ሰብለ ወንጌል እመ ንጉሥ ወታስተጸንእሙ በጥበብ ወምክር — ወትሜግቦሙ በሲሳይ ወበውሂበ ንዋይ ። ታሪክ ነገሥት ረ፩ ባለት ያላተ መው ገጽ 333

ግራኝ አህመድ ደረስጌ ባለበት ሰዓት ዓፄ ገላውዴዎስም በስሜን መቀመጣቸው ከስሜንም መላክተኛ ወደ ደባርዋ መላካቸው ከእስላሞቹ ጥብቅ ቍጥጥር የተነሣ አይቻልም ። ከደረስጌ (ስሜን) ተነሥቶ ግራኝ ወደ ትግሬ መሄዱ የፖርቱጋሎቹን መምጣት ሰምቶ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ክርስቶፎሮስ ያፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ሲያዘጋጁ የሰነበቱትን የመድፍና የጥይት የባሩድ መጫኛ ሠረገላ የበለጠ በማፋጠን ይሠሩ ዠመር ። ሥራውም እንዳለቀ ስምንቱን መድፎች በየሠረገላቸው ላይ ጭነው ሠረገላዎቹን ባሕር ነጋሽ ይስሐቅና ሌሎቹም ሹማምንት በቀረቡላቸው በሬዎች እያስጐተቱ እያስሞከሩ ሲዘጋጁ ሰነበቱ ።

በዚህ ጊዜ ግራኝ አህመድ ሰላይ እየላከ ሠፈራቸውን ያስመራምራል የሚሉ ወሬ ሰምተው ኖሮ ሠፈራቸውን በጥብቅ በዘበኛ ሲያስጠብቁ ሰነበቱ ። በዚሁ መካከል ክርስቲያን መስለው ሲሰልሉ የተገኙ ሁለት እስላሞች ተይዘው በክርስቶፎሮስ ፊት ከቀረቡ በኋላ ለመቀጣጫ እንዲሆኑ ብሎ በሠረገላ ተጐትተው እንዲበጣጠሱ ፈረደባቸውና በዚሁ ቅጣት ተገደሉ ።

ከዚህ በኋላ ከሐምሌ ወር (፲፭፻፴፫) እስከ ታኅሣሥ ወር (፲፭፻፴፬) መጀመሪያ ድረስ በዚሁ በደባርዋ ዝግጅቱ ከአለቀ በኋላ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በደንገጡሮቻቸውና በሃምሳ የፖርቱጋል ወታደሮች ታጅበው በስተኋላ የቀሩትንና መድፉን የጫኑትን ሠረገላዎች ይዘው ከፊት ቀድመው ሲጓዙ የጭነቱንና የጉዞውን ሁኔታ በደንብ መሆኑን ትጉሁና ብርቱው ክርስቶፎሮስ በሰጋር በቅሎ ተቀምጦ በአራት ባለበቅሎ ወታደሮች ታጅቦ በቀን ሁለት ጊዜ በሰልፉና በጉዞው ፊት እያለፈ ይመረምር ነበር ። በዚህ ዓይነት ሲጓዙ ከየአለበት ገበሬው ሁሉ እየመጣ በመግባት ሰዋቸው እየበረከተ ሄደ ።

ከስምንት ቀን ጉዞ በኋላ ባንድ የባሕር ነጋሹ ከተማ ደርሰው በዚያ የልደት በዓልን አከበሩ ። ከዚያ ተነሥተው ብዙ ጊዜ ወጣ ገባና ሠረገላ የማያስሄድ መጥፎ መንገድ እያጋጠማቸው መድፉ ከሠረገላ እየወረደና እየተፈታ በሰው ትከሻ ሆኖ ጉዞው ቀጠለ ። በዚህም ጊዜ ለጭፍራውና ለሕዝቡ መልካም ምሳሌ ለማሳየት ማዕርጉ ከፍ ያለው የሕንድ ጠቅላይ ገዥ ታናሽ ወንድም የሆነው ሹሙ ክርስቶፎሮስ ደጋግሞ የሚችለውን ያህል በጀርባው አዝሎ ይጓዝ እንደነበረ ካስታንሆሶ ከሌላው ታሪክ ጋር ስለሚተርክ ይህ የወጣት አለቃ የተጠቃውን የኢትዮጵያን የክርስቲያን ሕዝብ ከልቡ ለማገልገልና የሕዝቡን ጥቃትና ቍጭት ሊበቀል ቆርጦ እንደተነሣ ያስታውቃል ።

በዚህ ዓይነት ተጉዘው አጋሜ ግዛት ሲገቡ አገረ ገዥው ወገኖቹን ከድቶ እስላም የሆነ ኢትዮጵያዊ እንደነበረና የነርሱን መድረስ ሲሰማ ሸሽቶ ወደሌላ አገር እንደሄደ ፤ ባላገሩና የቀረው ሕዝብ ግን በፊት አገሩን ከሚገዙት እስላሞች ጋር ተስማምቶ ለመኖር የተቸገረበትን ምክንያት እያመለከተ ከንግሥቲቱ ዙሪያ መሰብሰቡን ከነርሱም ጋር የዚያ የሸሸው ሹም ወንድም ነበርና ባላገሮቹ እሱ ለወደፊት ይሾምልን ብለው አመልክተው ክርስቶፎሮስም ለንግሥቲቱ አግልዶ የአጋሜን

ISIC

ሹመት እንዳሰጠው በዚሁ በአጋሜ በጥር ፲፩ ቀን የሚውለውን የጥምቀትን በዓል እንዳከበሩ ጸሐፊው ካስታንሆዞ ይገልጻል (1) ።

በዚሁ ሠፈር እንዳሉ የግራኝ ጦር ያለበትን የአምባ ሠነይትን ተራራ በሩቁ ተመለከቱ ። በዛሬው ያገዛዝ ድልድል አውራጃው ዓድዋ ፥ ወረዳው አምባ ሠነይት ሆኖ ከተማው ነበለት ይባላል ። ያን ጊዜ ግን አምባ ሠነይት በአጋሜ ውስጥ ይሆን ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ክርስቶፎሮስ ስለአምባው ሁኔታ ሲጠያየቅ ፫ መውጫ ወደ አምባው መግቢያ እንዳለው ፥ እያንዳንዱም መግቢያ ተከላካይ ወታደር ከነአለቃው እንዳለበትና መውጫውም አስቸጋሪ የደንጊያ ቋጥኝና አለት የበዛበት መሆኑን ተገነዘበ ። ወደፊት ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ለመገናኘት ሲጓዝ ይኸን የግራኝ ጦር ያለበትን አምባ ሳያፈርስ ጉዞውን መቀጠል ቅር ስላለውና ይኸንኑ ለንግሥቲቱ ቢያማክር በዚህ በትንሽ ጦር አምባውን ለማፍረስ መሞከር አደገኛ ስለሆነ ጉዞውን ቀጥሎ ከወጣቱ ንጉሥ መገናኘት እንደሚሻል መከሩት ። እርሱ ግን በእግዚአብሔር ርዳታ ይኸን አምባ ለማፍረስ እንደሚችል ለንግሥቲቱ አረጋገጠና ከንግሥቲቱ አስፈቅዶ ጭፍራውን ይዞ ወደ አምባው አመራ ።

ከዚህ በኋላ በየበሩ የሚዋጋውን አለቃና ጭፍራ በደንብ እየለየ አሰልፎ ሲጨርስ የውጊያውን ትእዛዝ ሲሰጥ ሁሉም ወደየበሩ እየሄደ ውጊያውን ዠመረ በላይም ያሉት እስላሞች ቁልቁል ደንጊያ እየወረ[illegible]ናዳ እየሰደዱ ስላስቸገሩ እታች ያሉት ፖርቱጋሎች በመድፍና በጠበንጃ እየተከላከሉ ውጊያው ቀጠለ ። እስላሞቹ በደንጊያ ናዳ ሁለት ከመካከላቸው ሲገድሉባቸውና ማጥቃት ሊጀምሩ ሲሉ ከፊት ቀድሞ በጀግንነት የሚዋጋው ክርስቶፎሮስና ጭፍሮቹ ጨክነው በጠበንጃ በመዋጋት እስላሞቹን ጥሰው ከጫፍ ወደ አለው አምባ መዝለቅ ቻሉ ። ብዙም ጦርነት በየበሩ ተደርጎ ብዙ እልቂት ከሁለቱም ወገን ከሆነ በኋላ ወደመጨረሻው የአምባ በር ሲደርሱ ዓረቦች ያሉባቸው እስላሞች በኃይል ስለተቋቋሙ ፖርቱጋሎቹም እየፎከሩ እየተዋጉ ጨኸቱ ሲቀልጥ የእስላሞቹ አለቃ በዠግንነት እየተዋጋ በጦር ወርውሮ አንዱን የፖርቱጋል ተወላጅ ቢወጋው የጦሩ ጫፍ ባንድ ወገን ወጣ ሌላውን ደግሞ በጐራዴ ራሱ ላይ ቢለው የራስ ቁሩ ከራሱ ላይ በረረ የተመታውም ፖርቱጋል ከመሬት ላይ ወደቀ ። ይኸን አደገኛ ተዋጊ ሹም ሌሎች ፖርቱጋሎች ባዩት ጊዜ ፫ ሆነው ሂደው ደብድበው ከመሬት ዘረሩት ሲል ካስታንሆዞ ያስረዳል (2) ።

በሌላው በር የገጠሙትም እንደዚሁ በውጊያ አሸንፈው በመጨረሻ አምባው በሙሉ ተማረከ ። በዚህም ጊዜ ባለፈው ጦርነት ጊዜ የተማረኩ የክርስቲያን ሴቶችና የእስላም ሴቶች በየቤቱ ተገኙ ። በቅሎችና ፈረሶችም አገኙ ። ከድሉ በኋላ ሁሉም ሲሰበሰቡ ፰ ፖርቱጋሎች የሞቱ አርባ የቆሰሉ ሆነው ተገኙ ። በዚያ ያለውን መስጊድ ክርስቶፎሮስ ደጋግ በጳጳሱ "በቤርሙዴዝ" አስባርኮ ወደቤተ ክር

(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 7

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 16

ስቲያንነት ከአስለወጠው በኋላ ስሙን የድል መንሣት እመቤት አሰኝቶ በእመቤታችን ስም አሰይሞ ሚኞቹ ፖርቱጋሎች በዚያ ተቀበሩ ።

ከድሉ በኋላ ክርስቶፎሮስ ሁኔታውን እንድታይለት ለንግሥት ሰብለ ወንጌል ልኮ ነበር ። ነገር ግን መንገዱ ሁሉ ሬሳ ብቻ ነው ማለትን በመስማቷ ሳትሄድ ቀረች (1) ። ካስታንሆሶ የራሱ ወገኖች ምን ያህል እንደሞቱና ምን ያህል እንደቆሰሉ ሲጽፍ ከወዲህ ከነርሱ ጋር ሆነው የተዋጉትን የኢትዮጵያውያኑን የክርስቲያኖች ቍጥርና ከወዲያ የሚከላከሉትን የእስላሞች ቍጥር አልጠቀሰም ። ይሁን እንጂ ለማየትና በዚያ ለማለፍ ንግሥቲቱን እስኪያሰቅቅ ድረስ በመንገዱ ሬሳ ከሞላ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አልቋል ማለት ነው ።

በዠግንነት ሲዋጋ በጦርና በጐራዴ ሁለቱን ፖርቱጋሎች ከጨረሰ በኋላ ፫ ሆነው ሄደው የገደሉትን የእስላሞቹን ሹም ስም አለመጥቀሱ ያሳዝናል ። ይኸን ጊዜ በዓይፈርስና በሽምብራ ኩሬ ወይም በሌላ በብዙ የጦር ግንባር እንደነ አቡበከር ቀጢን እንደነነስረዲን የዋለ ብዙ የክርስቲያን የጦር ሹማምንት የፊጀ ሊሆን ይችላል ። እርሱም በዚያ በሸሸው ወገኖቹን ክዶ ከርሱ በታች በሚያገለግለው ኢትዮጵያዊ የበላይ ሆኖ የአጋሜን ግዛት ከግራኝ የተሾመ መሆን አለበት ።

ይህ በዠግንነት ተዋግቶ የሞተው የእስላሞቹ የጦር አለቃ መቼም ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ክርስቶፎሮስ ዴጋማ በደባርዋ መገናኘታቸውን ሳይሰማ አይቀርም ። ኃይሉን ቢተማመን ኖሮ ከአምባው ወርዶ በሜዳ ለመግጠም ባልተመለሰም ። ነገር ግን ከሰላይ እንደሚሰማው መድፍና ጠበንጃ ከያዙ የውጭ አገር ወታደሮች ካሉበት ከበረከተ ጦር ጋር ብቻውን ከመዋጋት ግራኝ ከደረሰኄ እስኪደርስለት ወይም ያንድ ሌላ የእስላም ጦር እስኪመጣለት በዚያው አምባው ላይ ሆኖ መቆየትንና ቀርጠው ሲመጡበት ብቻ መከላከልን መርጦ ይሆናል ።

ወጣቱ ክርስቶፎሮስ ደግሞ ይኸን የመሰለ ጠላት በጀርባው ትቶ ወደፊት ሲጓዝና ምናልባት ከግራኝ ወይም ከሌላ የጦር አለቃ ጋር ቢጋጠም ይኸኛው ከኋላ እንዳይገጥመው በፕላን አስቦ ጠላትን ከፊት እያጣሩ ወደፊት መሄዱ የተሻለ ነው የሚል ግምት አድሮበት ይሆናል ። የሆነ ሆኖ ቀድሞ ክርስቲያኖቹ በየጫካው በየተራራው ተደብቀው ሳለ ከሜዳ እየመጡ ከታች እስላሞቹ ሲወጉዋቸው ክርስቲያኖቹ ከላይ ናዳ እየሰደዱ ይከላከሉ የነበረውን አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ፍርዱን አዙሮ ፖርቱጋሎቹና ክርስቲያኖቹ ኢትዮጵያውያን ከታች አጥቂ እስላሞቹ ከላይ በናዳ ተከላካይ ሆኑ ። ይኸንንም የሠራ ከእግዚአብሔር ጋር የዕውቀትና የመሣሪያ ልዩነት መሆኑ የማይካድ ነው ።

የግራኝ ጦርና ፖርቱጋሎቹ በአምባ ሠነይት በዚህ ዓይነት እየተዋጉ ፖርቱጋሎቹ ሲያሸንፉ በየወረዳው ያለው ቀደም ብሎ በውዴታም በግዴታም ከአሸናፊዎቹ እስላሞች ጋር የነበረው ሕዝብ ከነሹማምንቱ እየመጣ ለንግሥት ሰብለ ወንጌል እየገባ ሰልፉ እየደረጀና እየበረታ ሲሄድ በበኩላቸው ወጣቱ ገላውዴዎስ

(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ገጽ 39

ባንድ ወገን ከመጡት እንግዶች ጋር መላላካቸው የግራኝንም ሁኔታ ማስለላቸው ሳይቀር በበኩላቸው የሠሩት ንጉሣዊና ወታደራዊ ተግባር ብዙ ሳይሆን አይቀርም።

እርሳቸው በትግሬም ሆነ በሸዋ ያደረጉት ሁሉ ብዙ ዝርዝር ታሪክ እንዳለበት የታወቀ ሆኖ ሳለ እንደ ዓረብ ፋቂህ ወይም እስካሁን እንዳነበብነው እንደ ደ ካስታንሆዞ ያለ ሰፋ አድርጎ ሊጽፈው የቻለ ባለመኖሩ በዚያው በታሪክ ነገሥት በግዕዝኛ ቋንቋ ባጫጭሩ የተጻፈውን በሚቀጥለው ምዕራፍ ተመልክተን ከዚያ በኋላ ወደነዚሁ ወደ ፖርቱጋሎቹ እንመለሳለን ።

## ምዕራፍ ፻፲፰

### ዓፄ ገላውዴዎስ ከስሜን ወደሸዋ ሄደው ከግራኝ አህመድ ልጅ ከነስረዲን (ናስር አድ - ዲን) ጋር እንደተዋጉ - በሸዋ የድል ጮራ መታየት (፲፭፻፴፩ ዓ. ም.)

ፖርቱጋሎችና የግራኝ አህመድ ጦር በትግሬ (አምባ ሠነይት) በዚህ ዓይነት ሲዋጉ በበኩላቸው ዓፄ ገላውዴዎስ ወደ ሸዋ ሄደው ከግራኝ አህመድ ልጅ ጋር የተዋጉትን ከመግለጹ ቀደም አድርጎ ባለፉት ምዕራፎች በዝርዝር ያመለከትናቸውን የወረራና የቃጠሎ ሰፊ ታሪክ ታሪከ ነገሥቱ በጥቂት መስመሮች እንደዚህ ሲል ያወሳል ።

ISIC

«በዚህ ዘመን አሸናፊነት በሰዓዲን በነበሩት የእስላም ተወላጆች እጅ ገባ ። እነርሱም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደልባቸው ሠለጠኑበት ፤ በኢትዮጵያ ምሥራቅና ምዕራብ ሰሜንና ደቡብ በተደረገው ጦርነት ሁሉ አሸናፊ ሆኑ ። በወርቅና በብር ከሕንድ አገር በመጣ የከበረ ደንጊያ ግድግዳቸው የተጌጠውን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉንም አፈራረሱዋቸው ። የሚበዛውንም ሕዝበ ክርስቲያን በሰይፍ ገደሉት ። ወጣቱንና ደናግሉን ልጁንና አዋቂውን በምርኮ እያጋዙ ለመጥፎ ሥራ ሸጡዋቸው ። በዚህ ጊዜ ብዙዎቹ ከክርስትና ሃይማኖት ወደ እስላምነት ዞሩ» (1) ።

ከዚህ በላይ ታሪከ ነገሥታችን የሚናገረው ትክክል ነው ። በዚህ ዘመን የሚለው ጦርነቱ ከተጀመረበት ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ጀምሮ ዓፄ ገላውዴዎስ ማሸነፍ እስኪጀመሩበት እስከ ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ድረስ በ፲፭ ዓመታት ውስጥ ያለውን ጊዜ ነው ። ድል አድራጊነት ሰዓዲን በነበረው እስላም እጅ ገባ የሚለው ከይፋት ጀምሮ እስከ ሐረር ያለውን አዳልና እስላም ነክ የሆነውን አገር አዳሎቹም እነሆ የኛም ጽሑፍ የሰዓዲን አገር ይሉታል ። በወላስሞች የዘር ግንድ ላይ እንደሚታየው ሰዓዲን (ሙሉ ስሙ መሐመድ አቡል ባራከት ሳድ አድ ዲን) ከዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋር

(1) ወበውእቱ መዋዕል ገብዓት መዊዕ በእደ ተንባላት ዘነበሩ በሰዓዲን ፤ ወተበውሑ ላእለ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊት ወሞዑ ኵሎ ጸብዓ ዘመንገለ ጽባሒሃ ወአረቢሃ ዘመንገለ ዱቡባ ወሰሜና እስከ አመዝበሩ ኵሎ አብያተ ጸሎት ዘሕንፃት አረፋቲሆን በወርቅ ወበብሩር ወአእባኒሃ ክቡራት ዘእምዕብነ ሕንደኬ ወቀተሉ መብዝሕቶሙ ለማሃይምናን . . . . የገላ. ዜ. መ. ገጽ 4 - 5

የተዋጋው የመሐመድ አርዌ በድላይ አባት ነው ። እርሱም ራሱ ባፄ ዳዊት ጊዜ ሲዋጋ ሞቷል ። ስለዚህ ሸዋ አንዳንድ ጊዜ ሸዋ በመባል ፈንታ የአምሃየስ አገር እን ደሚባል በዚሁ ዓይነት የአዳል አገር በማለት ፈንታ በዚህ በወላስማ ተወላጅ ስም የሰዓዲን አገር ወይም እንደዚሁ ሰዓዲን ይሉት ነበር ። በኢትዮጵያ በአራቱ ማዕዘን በተደረገው ጦርነት ሁሉ እስላሞቹ አሸናፊ ሆኑ የሚለውም ከዚህ በፊት እንዳመለ ከትነው አውቆ ወይም የውጊያ ሥፍራ በመለወጥ ካልተመለሰ በቀር ግራኝ አህ መድ ራሱ መሪ ሆኖ በአዋጋበት ሥፍራ ፖርቱጋሎቹ እስከመጡበት ጊዜ ድረስ ማሸነፍ እንጂ አንድ ጊዜም ተሸንፎ አለማወቁን ለመግለጽ ነው ። በወርቅና በብር ከሕንድ አገር በመጣ የከበረ ደንጊያ እየተጌጠ የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ አፈረሱት ያለውም እነዚያኑ ከዚህ በፊት ከዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ በዝርዝር ያነ በብናቸውን የነ መካነ ሥላሴን አብያተ ክርስቲያናት እየዘረፈ ማቃጠሉን ነው ።

ይኸን ከተረከበት ጽሑፍ ቀጥሎ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ግን ሃይማኖታቸ ውን ላለመለወጥ ረሃብን ፡ ጾምን ፡ ብርድን ፡ ዕርዛትን ችለው ካገር ወዳገር ከተራራ ወደ ተራራ መሰደዳቸውን የልጆቻቸውን የፊቅጦርን ሞት ፡ የሚናስን መማረክ ፡ ዓፄ ገላውዴዎስ ግን እናት ልጅዋን አቅፋ ከዱር አውሬ እንደምትጠብቅ እግዚአብ ሐር ጠብቆ እንዳቆያቸውና አሁን በዚህ ጊዜ እንደ ዳዊት ልጅ እንደ ሰሎሞን እው ቀትና ጥበብ አሟልቶ ገላውዴዎስን እንዳነገሣቸው ይገልጻል ። ከዚሁ አያይዞ አባ ትየው ዓፄ ልብነ ድንግል መጻሕፍተ ቅዱሳንን ያውቁ ስለነበር ይኸንኑ ዕውቀታ ቸውን ከወንድሞቻቸው ለይተው ያስተምሯቸው እንደነበረ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ተገ ልጦላቸው ከኢየሩሳሌም እግዚአብሔር በሚልክላቸው የብረት ዘንግ ጠላቶቻቸ ውን ቀጥቅጠው እንደሚገዙ አባትየው በትንቢት ታይቶአቸው እንደነበረ ይገል ጻል ። ግዕዙ ከኢየሩሳሌም እግዚአብሔር በሚልክለት የብረት ዘንግ (በትረ ሐጺን) ጠላቶቹን ይቀጠቅጣል የሚለው ምናልባት ባለፈው እንዳነበብነው ወደፊትም እንደምንመለከተው በፖርቱጋል ንጉሥ ፈቃድ የመጡትን ፬፻ የፖርቱጋል ወታደ ሮች ይዘው ዓፄ ገላውዴዎስ ግራኝ አህመድን ከነጦሩ ማሸነፋቸውን ማውሳቱ ይሆ ናል ። እንደዚሁም ከመንፈሳዊው ትምህርት ቀጥሎ ዓፄ ገላውዴዎስ እንደ ነገሥ ታት ልጆች ደንብ ፈረስ ግልቢያን ፤ አደንን ፤ ቀስት አወራወርን ፤ የጦርነት ትምህ ርት ተምረው ስለነበረ በዚሁ በተማሩት ከነገሡ በኋላ ከዚህ በፊት ባለፈው ምዕ ራፍ ያነበብነውን ጦርነት ተዋግተው እንዳሸነፉ ያመለክታል ።

እንደ ነገሥታት ልጆች ውኃ ዋና ፡ ፈረስ ግልቢያ ፡ አደን የጦር ትምህርት ተማሩ የሚለው አብዛኛው የተለምዶ አነጋገር ነው እንጂ የኚህ ንጉሥ ዕድሜ ከነገ ሡበት ከ፲፰ ዓመት ዕድሜያቸው ውስጥ ፲፭ ዓመት ከአባታቸው ጋዝ ጋር ካገር ወደ አገር በመሸሽ ያለፈ ጊዜ ስለሆነ በዚህ በስደትና በመከራ ዘመን ተዝናንተው የውኃ ዋና የፈረስ ግልቢያ የአደን ትምህርት እየተሰጣቸው ለማደግ የመከራው ጊዜ ፈጽሞ ሊፈቅድ የሚችል አይመስልም ። ነገር ግን ከሰላም ጊዜ ይልቅ የሰው ልጅ በመከራና በጦርነት ሰዓት ብዙ ነገር በተለይ ጦርነትን ትዕግሥትን እንደሚ ማር የታወቀ ነው ። በሰላምና በጸጥታ በተድላና በደስታ መካከል ካደገ ወጣትም

መከራና ስደትን ረሃብንና ችግርን የለመደ ሰው የበለጠ ጠንካራና ታጋሽ ይሆናል ። ስለዚህ ዓፄ ገላውዴዎስም ከልጅነታቸው ዠምሮ ሕይወታቸው ያለፈው እንደ ዕድል ሆኖ ግራኝ አህመድ በወረረበት ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ግዛቱ በጸናበት ባ፲፭ቱ ዓመታት መካከል ስለሆነ ይኸው መጥፎ ጊዜ የርሳቸውን የወጣትነት ዕድሜ በደንብ እንጾ አባታቸው ከሞቱ በኋላ ዙፋኑን ለመቀበል ሁል ጊዜ ድል ለመ ሆን ተስፋ የቆረጠውን ክርስቲያናዊ ሕዝብ ወደ ድል አድራጊነት ለመምራትና በአሳባቸውና በተግባራቸው እንዲጸኑ አድርጓቸው ይሆናል ።

ከላይ ከቆመበት ዠምሮ ታሪክ ነገሥቱ ከነገሡ በኋላ ከሠራዩ ወደ ስሜን ከስ ሜን (ቤገምድር) ወደሸዋ መሄዳቸውን በዚያም በተከተላቸው ትንሽ ጦር ግራኝ ሾሞ በደዋሮ ከአስቀመጠው ከልጁ ከነስረዲን (ናስር አድ - ዲን) ጋር መዠመሪያ ተዋ ግተው መሸነፋቸውን ቀጥሎ በይፋት መልሰው ማሸነፋቸውንና ከዚያ በኋላ በሕ ዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ደስታ ሆኖ ቀድሞ የሰለሙት ሁሉ ወደ ክርስቲያንነት መመ ለሳቸውን በዚሁ በግዕዝኛው እንጋገር ይገልጽልናል ።

ባለፈው እንዳመለከትነው በግራኝና ባፄ ልብነ ድንግል መካከል በመጨረሻ ዎቹ ዓመቶች የተደረጉትን የጦርነት ታሪኮች በዝርዝር እንዳንመለከት የዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ በ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. በተደረገው በጣና ሐይቅ ከገሊላ ገዳም ብዝበዛ ላይ ስለቆመ ዓፄ ገላውዴዎስ በትግሬ በስሜንና በሸዋ ከግራኝ ልጅ ወይም ከሹማ ምንቱ ጋር ያደረጉትን ጦርነት ሰፋ ባለ ሀ[illegible] ልናነብ አልቻልንም ። ስለዚህ ከገ ዳመ ገሊላ ዘረፋ ወዲህ እስከ ግራኝ አህመድና እስከ ዓፄ ገላውዴዎስ ሞት ድረስ ላለው ታሪክ መሠረታችን የደንበኛ ጸሐፊውን ስም የማናውቀው የታሪክ ነገሥት ጽሑፍና በተረፈ ባለፈው ያነበብናቸው የፖርቱጋሎቹ የዮሐንስ ቤርሙዴዝ የእነ ሚካኤል ደ ካስታንሆዞ መጻሕፍት ናቸው ።

ዓረብ ፋቂህ በመጽሐፉ ላይ ለግራኝ አህመድ ነስረዲን (ናስር አድ ዲን) የሚ ባል ልጅ እንደነበረው ይኸም ልጁ በደዋሮ ተሾሞ ያስተዳድር እንደነበረ አይናገ ርም ። በታሪክ የታወቀ አሊገራድ የተባለው ከድል ወንበራ የተወለደው ነው ። ሌላ ደግሞ መሐመድ የሚባል ግራኝ ከሞተ በኋላ የባሕር ነጋሽ አባት ይዞት የገባውና ከአቤቶ ሚናስ ጋር ለውጥ ተደርጎ ወደ አገሩ የተመለሰውን እናውቃለን ። ሁለተኛ የተክለ ሃይማኖት ሚስት የነበረችውን ባኒን ማርኮ እንደመታያ አድርጎ ለአደን ሱልጣን ከላከው በኋላ ሚስቱን ለራሱ ዕቁባት አድርጎ እንደ አስቀራት እርሷም ወንድ ልጅ እንደወለደችለት ተጽፏል ። ነገር ግን ከእርሷ የተወለደው ልጅ ተክለ ሃይማኖት በተማረከ ባመቱ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ላይ ስለሚሆን በአሁኑ ዓፄ ገላውዴ ዎስ በነገሡ በ፪ኛው ዓመት በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ዕድሜው አሥር ዓመት ብቻ ስለሚ ሆን በሞግዚት ካልሆነ በቀር በዚህ ዕድሜው ደዋሮውን ያህል አውራጃ እየገዛ ጦር እየመራ ከዔ ገላውዴዎስ ጋር መዋጋትና ማዋጋት የሚችል አይመስልም ።

ይሁን እንጂ ግራኝ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ለፖለቲካ ማሠሪያና ለዘመድ ማፍሪያ ሲል አንድ ጊዜ የሐድያውን ሁለተኛ የመዘጋውን ባላባት ልጅ ማግባቱን ስለምናውቅ እንደዚሁ የኢትዮጵያን ወረራ ከመዠመሩ በፊት ከዋናይቱ ሚስቱ

ከድል ወንበራ በቀር ከአዳልና ከሱማሌ ወይም ከወላስሞች ውስጥ ያስቀመጣቸው ዕቁባቶች ስለማይጠፉ ነስረዲን ምናልባት ከነዚህ ያንደኛዪቱ ልጅ ሊሆን ይችላልና አሁን ወደ ዋናው ታሪክ እንመለስ ።

በግራኝ አህመድ ወረራ ምክንያት ዓፄ ልብነ ድንግል በሞቱበት በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. መስከረም ፳ ቀን ላይ ንጉሣዊው ቤተ ሰብ ባንድነት በደብረ ዳሞ የነበረ ይመስላል ። በዚህ የግራኝ ጦር ለመውጣት በማይችልበት ተራራ የንጉሡን ቀብር ወግና ማዕርግ የሌለውን የአጭር ጊዜ ኀዘን ባንድነት ከአሳለፉ በኋላ ዓፄ ገላውዴዎስ በዚያው በተራራው ላይ ሥርዓተ ንግሡ እንደ ነገሩ ተፈጽሞላቸው ወደታች ወርደው ጦር አጠራቅመው እስካሁን በነበረውና ከንጉሡ ባልተለየው ሠራዊት ላይ ጨማምረው በትግሬ ከነአብሳማ ኑር ከነ ድልበ ኢየሱስ ሲዋጉ ሲሸነፉና ሁኔታው አደገኛ ሲሆንባቸው ወደ ስሜን ተራራ እየሄዱ ሲደበቁ ቆይተው የ፲፭፻፴፫ ዓ. ምሕረትን ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ባሁኑ ጊዜ (፲፭፻፴፬ ዓ. ም.) ከነስረዲን ጋር ተዋግተው አንድ ጊዜ ሲሸነፉ አንድ ጊዜ ሲያሸንፉ በይፋት ተራራ ይገኛሉ ።

እናትዮዋ ሰብለ ወንጌል ግን ባላቸውን ከቀበሩ በኋላ በዚህ በአስፈሪው ሰዓት በዚያው በደብረ ዳሞ ተራራ ከልጆቻቸውና ከጓዛቸው ጋር ከመቀመጥና መጭውን ጊዜና ዕድል ከመጠባበቅ በቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ። በጸሎታቸውም እን ደባላቸው አደራህን በጠላቴ በግራኝ አህመድ እጅ አትጣለኝ ከምትጥለኝ እንደ ባሌ ግደለኝ እያሉ ወደ እግዚአብሔር ሳይጸልዩ አይቀርም ። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሞቱም ከምርኮውም ጠብቆ ለርዳታ ከመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር ተገናኝተው ፲፭ ዓመት ሙሉ ካገር ወደ አገር እያሳደደ መከራ ያሳያቸውን የጠላታቸውን ውድቀት አሳያቸው ።

ወጣቱ ዓፄ ገላውዴዎስ በወጣትነት እእምሮአቸው ላይ የተሳለው የግራኝ ወረራ የመኳንንቱ እልቂት የአብያተ ክርስቲያኑና የቤተ መንግሥቱ መዘረፍና መቃጠል የአባታቸውና የእርሳቸው የማያቋርጥ ሽሽት የግራኝ አዘንግቶ መዋጋት የንጉሣዊው ቤተ ሰብ መዝረክረክ የወንድሞቻቸው የሚናስ መማረክ የፊቅጦር ሞት መሆን አለበት ። ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ንዴቱም ኀዘኑም እንደ እሳት ሲያቃጥላቸው የኖረው አሁን ባባታቸው እግር ዘውድ ጭነው የበላይ ኃላፊነት ከሚሰማቸው ጋር የወጣትነት ድፍረት ተደርቦ በትግሬ ግዛት ተዋግተው ከዚያ ደግሞ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የግራኝ ሥልጣን በተዘረጋበት ሰዓት ከስሜን ተነሥተው በእንጎት በቤተ አምሐራ ወይም ታቹን በጐጃምና በዳሞት አልፈው የአባቶቻቸው የነገሥታቱ መቀመጫ ወደ ነበረው እርሳቸውም ወዳደጉበት ወደ ሸዋ ተመልሰው ከግራኝ ልጅ ጋር በድፍረት መዋጋታቸው አስደናቂ ነው ።

በዚህ ጊዜ የነበራቸውን ጦር ታሪክ ነገሥቱ በ፰ ወይም በ፸ ፈረሰኛ በትንሽ የእግረኛ ጦር ላይ መድቦት ስለሚገኝ በዚህ ጊዜ የሚያደርጉት ጦርነት የደፈጣ ጦርነት ሊሆን ይችላል ። በዚህም ላይ በመላላክ ጭምር ምንጊዜም አልፎ አልፎ ውጊያውን ያላቋረጠውን የሸዋን ሕዝብ የጠቅላላውን የልብ ድጋፍ ያንዳንዶቹንም አብሮ ዘማችነት አግኝተው ይሆናል ። ይኸውም ሆኖ ሚዳማ በሆነው በደ

ዋር ግዛት ሳይቀናቸው ቀርቶ ተራራማ ወደሆነው ወደ ይፋት ተዛውረው በየአለፉ በት ተሰፋ ቀርጦ የነበረውን ሕዝባቸውን በመላላክ እየቀሰቀሱ የይፋት ሰዎች ይኸ ውና ማለት ከየአለበት ተጠራቅሞ ይፋት የሚገኘው ተዋጊ ከአገር ተወላጁ ጋር በንጉሡ ዙሪያ ተባብረው ወጣቱን ንጉሥ በመርዳት በናስር አድ ዲን በሚመራው ጦር ላይ አደጋ እየጣሉ ፊት ለፊትም እየገጠሙ እስከማሸነፍ ደርሰዋል ማለት ነው ።

ስለዚህ ጉዳይ ደንበኛው ታሪከ ነገሥት በተለመደ ግዕዝኛ አነጋገር ፣ በመጀመሪያው ጊዜ በመከራ ከመኖር በክብር መሞት ይሻላል በሚል ስሜት ፳ ወይም ፴ የሚሆኑ ፈረሰኞችና እንደዚሁ ናጥራቸው ያነሱ ወታደሮች ይዘው ፩ሺ ፈረሰኛ ፲ሺ እግረኛ ከያዘው ከነሰረዲን ጋር ተዋግተው ሳለ እርሳቸው መሸነፋ ቸውንና ከሰዎቻቸው ብዙዎቹ መሞታቸውን ይገልጽና ቀጥሎ በእርሳቸው ላይ የሰው ሁሉ ሕይወት የተያዘ በመሆኑ እግዚአብሔር ጠብቆ እንዳዳናቸው ፣ ከደዋ ሮው መሸነፍ ወዲህ ሰው ሁሉ በርሳቸው ተስፋ ያደርግ የነበረውን ለመፈጸምና በእስላሞቹ ላይ የገበሬና የአርበኛ ወታደራቸውን ይዘው ገጥመውት ነስረዲን እን ደተሸነፈ ከሠራዊቱም በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን እንደገደሉበትና መንግሥት ወደር ላቸው እንደዞረ ያመለክታል ። በመጨረሻም ነስረዲን ከዚህ መሸነፍ በኋላ ወገ ኖቹ መርዝ አጠጥተው ገደሉት የሚል ወሬ ሮስማቱን ጸሐፊው ያስታውሳል (1) ።

እርሳቸው በሸዋ ከግራኝ አህመድ [illegible] በሚዋጉበት ሰዓት በምጥዋ በኩል የመጡት ፖርቱጊዞች ምጥዋ ደርሰው ከምጥዋ ደባርዋ ከደባርዋ እምባ ሠነይት አልፈው ከግራኝ ጦር የተዋጉበት ጊዜ ነው ። በዚህ ምክንያት ንግሥት ሰብለ ወን ጌልና ክርስቶፎሮስ ደጋማ ካዬ ገላውዴዎስ ደብዳቤ የደረሳቸው ከዚሁ ከይፋት መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

ስለዚህ የግራኝ ሰላይ በያለበት እንደመብዛቱ መጠን ፖርቱጋሎቹ በአጋሜ ዓዬ ገላውዴዎስ በሸዋ መዋጋታቸው አንዳንድ ጊዜም ማሸነፋቸው ከግራኝ ስለማ ይሠወር የገላውዴዎስ ጦርና የፖርቱጋሎቹ ወታደሮች እንዳይገናኙ በያለበት መን ገዱንና መተላለፊያውን ማስጠበቁ የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ ያለፈውን ቍጥ ጥር አልፈው ከሰሜን ወደ ሸዋ እንደመጡ አሁንም ከሸዋ ተመልሰው ወደ ሰሜን ለመድረስ ላዬ ገላውዴዎስ አልተሳናቸውም ። በትግሬ በኩል ፖርቱጋሎቹ ያስገ ኙት የእምባ ሠነይት ድል የድል መጀመሪያ እንደሆነ በሸዋም የይፋቱ ድል ለክር ስቲያኖቹ ዋና የተስፋ ጮራ መሆን አለበት ። ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ይኸን የመሳ ሰለ የድል ጮራ ከፈነጠቀ በኋላ መልሶ እንደ ሰቀቀን የጠፋበት ጊዜ አለ ። ለምሳሌ

(1) እሜሃ ኮነ ንጉሥ ነስረዲን ወልደ አህመድ በድባሒሃ ለኢትዮጵያ ዘትሰመይ ደዋሮ በፈቃደ እቡሁ ወሎቱ ብዙኃ ሠራዊት መጠነ ፲ቱ፻ መስተጽዕናነ አፍራስ ወእልፍ እጋር ። ወኢኮነ ለግር ገላውዴ ዎስ ዘይበዝሕ እም ፳ አው እምነ ፴ አፍራስ ወአጋራውያኒሁ ከማሁ ውሁዳን ወእምብዝኃ ትን ዓቱ ለቤተ ክርስቲያን ...... ዓዋብዓ ይፃባዕ ምስለ ተንባላት .... ወቀተሉ ዓበይተ እምሠራ ዊቱ ። ኮንዘልማን ያላተመው ዜና መዋዕላቸው ገጽ 12 – 13

፭ኛ. የግራኝ ዋና ዋና የጦር አለቆች ገራድ አህሙሽና ገራድ ማታን ቢን ኡስማን በ፲፭፻፵፫ ዓ. ም. አምባ ግሼንን የከበቡ ጊዜ እነቢትወደድ ሠርፄ ተዋግተው የሱማሌዎቹን ጠቅላይ አለቃና የግራኝ አማች የነበረውን ገራድ ማታንን ከጦርነቱ ላይ ገድለው ጭንቅላቱን ቆርጠው ዋናውን መሪ አህሙሽን ከነ ሕይወቱ ማርከው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የቀረቡ ጊዜ ታላቅ ደስታ ተደርጎ ነበር ። በያለበት በሚያደርገው እልቂት አስለቃሽ የነበረው ግራኝ አህመድ ስለአማቹ ስለገራድ ማታን ሞት ራሱ አልቃሽ ሆኗል ።

፮ኛ. ወዚር አዶሌ ለግራኝ አህመድ አብሮ አደጉና ሞግዚቱ በዚህም የጦርነት ሰዓት ዋና የቀኝ ክንዱና ታማኝ ከፍተኛ የጦር አለቃው እንደነበረ ባለፉት ምዕራፎች በሰፊው አንብበናል ። በ፲፭፻፵፪ ዓ. ም. በሰኔ የላስታና የትግሬ ግዛት በተወረረበት ሰዓት የሠራዊው ሹም (አቃጅነ ሠራዊ) ተስፋ ልዑል ወዚር አዶሌን ገድሎ ጭንቅላቱን አስቆርጦ ለዓፄ ልብነ ድንግል ግዳይ በጣ ለላቸው ጊዜ አዶሌ ከሞተ የግራኝም መጥፊያ ደረሰ ተብሎ ነጋሪት እየተ መታ ጥሩምባ እየተነፋ የዚህ ሰው ሞት በታላቅ ክብረ በዓል መከበሩን በዚሁ በዓል ላይ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ዋናው የጦር አለቃ ደገልሃን እናንት መነኮሳትና ዲያቆናት መኳንንትና ቀሳውስት አዶሌና ሹማምንቱ መሞታ ቸውን አወቁ እንግዲህ የኛ ክብር የእስላሞች ጎሣር መዠመሩን ተገንዘቡ ያለውን አንብበናል ። ዳሩ ግን የአዶሌ ሞት ቀጥሎ ባለው ጊዜ የጦርነቱን ቀንበር አላቀዘቀዘውም ። ለክርስቲያኖቹም በአዶሌ ሞት ተፈንጥቆ የነበ ረው የድል ጮራ በገዳዩ በተስፋ ልዑል ሞት ተመልሶ ደንግዟል ። እንዲያ ውም ከዚህ ቀጥሎ ጋብቻ ጠይቆ የእምቢታ መልስ ካገኘ ወዲህ ባዔ ልብነ ድንግልና በቤተ ሰባቸው ላይ የደረሰውን ባለፈው አንብበናል ።

አሁን ደግሞ በይፋት የወለደው ልጁ ናስር አድ ዲን በውጊያ ሲሞት በአምባ ሠነይት ፖርቱጋሎቹ ሲያሸንፉ ዘለቄታ ያለው የደኅንነትና የትንሣኤ ተስፋ በክር ስቲያኖቹና በወጣቱ ንጉሥ ዘንድ መቅረቡ እንደሚገመት የታወቀ ነው ። ነገር ግን ከሥር ወረራውን የወጠነውና ውጣኔውን ወደ ፍጻሜ ያደረሰው ራሱ ግራኝ አህ መድ በሕይወት እስ ድረስ በሹማምንት ሞት ላይ የሚጣለው ተስፋ ሁል ጊዜ ጉዶሎ ከመሆን አይዘልም ። ሹማምንት ቢሞቱ ሹማምንት ይተካሉ ። ወዚር አዶሉ ቢሞት ገዳዩን ተስፋ ልዑልን የገደለው ወዚር አባስ በአዶሉ ሥፍራ ተተክቶ ለግ ራኝ እንደምክትሉ ሆኖአል ። ግራኝ አህመድ ግን ምትክ የለውም ። በትጋቱና በዠ ግንነቱ በተንኮሉና በክፋቱ በአጥቂነቱና በዘዴው በጠቅላላው በስመ ጥሩነቱ በነ ዚሀ ፲፭ ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜም ሳይሸነፍ እያከታተለ በሚያገኘው ድል አድ ራጊነትና በጽኑ ገዥነቱ ምክንያት እርሱ ከመሞቱ በፊት የክርስቲያኖቹ የድል ተስፋ ወደ ፍጹምነት አይመጣም ። ከሞተ በኋላ የሆነውን ስንመለከት በእውነ ትም የኢብራሂም ልጅ ይማም አህመድ ከኋላውም ከፊቱም ተተኪ የሌለው ልዩ ችሎታ በፍጥረቱ ያለው መሪ ሆኖ እናገኘዋለን ። እንደርሱ ያለ መሪ ሁል ጊዜ ሲሞት እርሱን የመሰለ ተተኪ በዓለም ታሪክ ውስጥ እምብዛም አያጋጥምም ። እስ

ከንድርም ናፖሊዎንም አላገኙም ። ስለዚህ ነው የእሳት ልጅ አመድ የሚባለው ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥትን ትንሣኤ የሚያረጋግጠው የራሱ የግራኝ ሞት ስለሆነ ወጣቱና ደፋሩ ንጉሥ ገላውዴዎስ ወደ ሸዋ መጥተው ልጁን ነስረዲንን በማሸነፍ በመጠነኛ ድል የደጎንንት ጊዜ መቃረቡን ለሕዝብ ካበሰሩ በኋላ ዋናው የመንግሥታቸው ጠላት ወደሚገኝበት ወደ ትግሬ ተመለሱ ።

ከሸዋ ወደ ትግሬ ሲመለሱ ከዚህ በፊት ከምጥዋ ተልኮ ወደርሳቸው ከነክርስቶፎሮስ ደብዳቤ ይዞ የመጣው አሪያስ ዲያዝ የሚባለው አብሮአቸው እንደነበረ ዜና መዋዕሉ ያረጋገጠውን ከዚህ በፊት አንብበናል ። እርሱም ከክርስቶፎሮስ ደጋማ ሞት በኋላ አልፎንስ ካልዴይራ ተሾሞ ሳለ ይኸኛውም ስለሞተ ከግራኝ ሞት በኋላ ወደፊት እንደምናነበው ከካቶሊክነት ወደ ተዋሕዶነት ዞሮ ስሙም ማርቆስ ተብሎ ከሞት በተረፉት ፖርቱጊዞች ላይ አልቅና ተሾሟል ። እርሱም የፖርቱጋልና የሕንድ ክልስ ነው ይባላል ።

ይሁን እንጂ ዓፄ ገላውዴዎስ ከሸዋ ወደ ትግሬ ሲሄዱ ግራኝ አህመድ ሁለቱ ወገኖች እንዳይገናኙ ባደረገው ቍጥጥር ምክንያት ንጉሡ ወደ ትግሬ በቀጥታ በመሄድ ፈንታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ስሜን ስለሄዱ ፖርቱጋሎቹና ዓፄ ገላውዴዎስ ከመገናኘታቸው በፊት በሚያስደስት አኳኋን ፖርቱጋሎቹ ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ይዘው በአምባ ሠነይትና በስሀርት አከታትለው ካሸነፉ ወዲህ በሚያሳዝን መንገድ አሸንጉ ሐይቅ አጠገብ በተለይ ወፍላ ላይ ፖርቱጋሎቹ ተመልሰው ተሸነፉ ፣ ዋናው መሪ ክርስቶፎሮስም ተማርኮ ተገደለ ። የተረፉት ፖርቱጊዞች ካዒ ገላውዴዎስ ጋር ተገናኝተው ኍራቸውን አጠንክረው በተዋጉ ጊዜ የማይሸነፈው ግራኝ ተሸንፎ ጥይት ጅንደ ትንኝ አይቀነቅነውም ተብሎ የተተረተለት ሰውዬ ባንዲት ጥይት ተመትቶ ይወድቅና ይሞታል ። ዝርዝር ታሪኩ የሁሉም በየተራ በሚቀጥለው ምዕራፍ ይቀርባል ።

## ምዕራፍ ፻፲፮

## ግራኝ አህመድና ክርስቶፎሮስ ደጋማ በመናናቅ የተመላለሱት ደብዳቤ

ፖርቱጋሎቹ ምጥዋ ከገቡበትና ደባርዋ ከከረሙበት ይልቁንም አምባ ሠነይት ላይ ድልን ከአገኙ ወዲህ በተለይ ደግሞ ራሱ ክርስቶፎሮስ እንደገመተው የንግሥት ሰብለ ወንጌል በመካከላቸው መገኘት ከየአለበት ብዙ ሕዝብ ስቦ ኍራቸው የጸና ሆኗል ። በዚህ ዓይነት ግማሹ በደስታ እየመጣ ሲገባላቸው የቀረው ደግሞ ከግራኝ ጋር ሆኖ አገሩንና ወገኑን በጣም ከመበደሉ የተነሣ ምሕረት አያደርጉልኝም ብሎ ወይም አሁንም ቢሆን ግራኝ አህመድ ሊሸነፍ አይችልም በሚል ግምት እያወላወለ ሲሸሽ ሁኔታው ልክ በኢጣልያ የወረራ ፍጻሜ ዘመን በ፲፱፻፴፫ - ፴፬ ዓ. ም. ከደረሰው ጋር ተመሳሳይ ነው ። ባንድ ወገን ግማሹ ባንዳና ሾማምንት ከኢጣልያ ጐን ሆኖ የአጭር ጊዜ ኑሮውን ሲቀጥል የቀረው ከጠላት ጋር የነ

ISIC

በርነው ፤ የፋሽስት መንግሥት አስገድዶን ነው ባዩ ብዙ እንደነበረ አሁንም በዚህ ጊዜ የቀረው ሕዝብና ሹማምንት ወደ ግራኝ የገባነው ወይም ለግራኝ የገበርነው የም ንሄድበት አጥተን በመቸገር ነው እያሉ ምሕረት በመለመን ወደ ንግሥቲቱ እየገ ቡና ይቅርታ እያገኙ ሹመታቸውን እያስመረቁ ግራኝን ለመውጋት ተዘጋጅተ ዋል ። ንግሥት ሰብለ ወንጌልም ቀድሞውኑ በመከራው ጊዜ በተለይ ፈጽሞ አገራ ቸውን ያልከዱትንና አንዳንድ ወሬ በምሥጢር ያቀብሏቸው የነበሩትን ሹመታቸ ውን እያጸደቁ የወደፊቱ ጦርነት በደንብ እንዲዘጋጅ አደረጉ (1) ።

ከዚህ በኋላ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በአጋሜ ሳሉ በእምባ ሠነይት ጦርነት የቆ ሰሉትን ሲያስታምሙ ክርስቶፎሮስም እስካሁን ስላገኘው ድል ለንጉሡና ለወን ድሙ ለሕንድ እንደራሴ ለመላክ በምጥዋ በኩል እየተላላከ ባንድ ወገን ግራኝ ያሰ በትን ሥፍራና የያዘውን ጦር ሲያስልል ሰብንቶ ቀጥሎ ከአጋሜ ወደ እንደርታ በርሱ አነጋገር ወደ ያርቲ ሜዳ እንደመጡ ደ ካስታንሆዞ ያመለክታል ።

ይህ ካስታንሆዞ ያርቲ ያለው አገር እንደ ሙሴ ሊትማን አገማመት ከእንደ ርታ ጋር የሚዋሰነው አጀርት (ዋጅራት) ወይም ሰሀርት ይሆናል ያሉት በትክክል የሚመስል ነው ። ሰሀርት ከዋጅራት ሰሜን ከግባ ወንዝ በደቡብ ፤ ከእንጣሎ ምዕ ራብ ላይ የሚገኝ ነው ። የሆነ ሆኖ በዚህ ሠፈር በደረሱበት ጊዜ የግራኝ ጦር ብዙ ስለሆነ እኔም ይኸው ወደናንተ በመጓዝ ላይ ነኝና ከመድረሴ በፊት ጦርነት ከግ ራኝ ጋር እንዳትገጥሙ የሚል ያዓ ገላውዴዎስ መልእክት መድረሱን ጸሐፊው ያረ ጋግጣል (2) ። የራሱ የክርስቶፎሮስና የባሕር ነጋሹ ይልቁንም የግራኝ አህመድን ውጊያና ብርታት ከብዙ ዘመን ጀምረው ደህና አድርገው የሚያውቁት የንግሥት ሰብለ ወንጌል አሳብ በግራኝ የሚመራውን ጦር ከመግጠም በፊት በተቻለ መጠን በሌላ መንገድ እያቋረጡ አልፎ ካፄ ገላውዴዎስ ጋር መገናኘትን ነው ።

ዳሩ ግን ሳይታሰብ የግራኝን ብዙ ጦር ይዞ የመቃረብ ወሬ ለስለላ የተላኩት ሰዎች አመጡ ። በዚህ ጊዜ ንግሥቲቱ አሁንም ቢሆን መጋጠሙ ቀርቶ በሌላ መን ገድ ዞሮ ከገላውዴዎስ መገናኘት የሚሻል መሆኑን አጥብቀው አሳሰቡ ። ይሁን እንጂ የ፳፮ ዓመቱ ወጣትና ዝግናው ክርስቶፎሮስ ከግራኝ ፊት መሸሽ ከዝግን ነቱ መንፈስ ጋር ካለመስማማቱ በላይ እስካሁን በተሰበሰበው ሕዝብና መኳንንት መካከል ያገኘውን የአሸናፊነት ዝና የሚያበላሽበት መስሎ ስለታየው ይሁን ወይም ያለ ንጉሡ ብቻውን በመዋጋት የአሸናፊነትን ክብር ለራሱ ለመቀዳጀት ተመኝቶ ይሁን ለውጊያ ቆርጦ ተነሣ ። ወደ ንግሥቲቱም ሠፈር ሄዶ በፈገግታ መልክ እነጋግሮ የግራኝን ጦር በደንብ ለመከላከል የሚችል መሆኑን አረጋግጠ በማጽናናት እሺ አሰኛቸው ።

ከዚህ በኋላ የሁለቱ ጦር ሠራዊት በሩቁ እየተያየ ሲሰላለል በሰነበተበት ሳም ንት ከዚህ በፊት በ፲፰፻፷፰ ዓ. ም. ለሽምብራ ኩሬ ውጊያ ብዙ ጦር ያስከተሉት ዓፄ ልብነ ድንግል ግራኝ አህመድን ከነጦሩ እንዳያመልጧችሁ ሁሉንም ከበሏ

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕራፍ 11
(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕራፍ 12 ገጽ ቍጥር 34

ቸው ይሉበት በነበረው የንቀት ስሕተት ግራኝ አህመድ በአሁኑ ሰዓት እንደወደቀ
በት ታሪኩ ያሳያል ። በንቀታቸው ዓፄ ልብነ ድንግል ከ፲፫ ዓመታት በፊት በሽም
ብራ ኩሬ የገጠማቸው የመሸነፍ ውርደት በዚህ ጦርነት ላይ ስለደረሰበት ሰሎሞን
በምድር አዲስ ነገር የለም ያው የሆነው ተመልሶ ይደረጋል ያለው ምንጊዜም ትክ
ክል መሆኑን እንመለከታለን (1) ።

ስለዚህ ግራኝ አህመድ ጦርነቱን ከመዠመሩ በፊት በክርስቶፎሮስ ዱጋማ
ወጣትነት በፖርቱጋሎቹ ወታደሮች ዝቅተኛ ቍጥር (፬፻) እርሱን በእንደዚህ ያለ
አነስተኛ ጦር ለመግጠም በመድፈራቸው ከመገረምና ከመሳለቅ ጋር ራሱን እንደ
ማይበገር ንጉሥ በመቁጠር በዚህ ሁሉ ምክንያትና በዚህ አነስተኛ የልጅነት
ዕድሜ ባለው ወይም በሴት ንግሥት "ሰብለ ወንጌል" ከሚመራ ዝቅተኛ ጦር ጋር
መግጠሙን ከውርደት ስለቆጠረው እንደተሰለፈ ገሥግሦ ጦርነቱን በመክፈት
ፈንታ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የመሳለቂያ ቃል ጽፎ በደብዳቤ ለክርስቶፎሮስ እንደ
ላከ በሥፍራው የነበሩት ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞና ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በየግል
መጽሐፋቸው ያመለክታሉ (2) ። የደብዳቤው ቃል በጸሐፊው በካስታንሆዞ አነጋ
ገር ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

«ይቺን ታህል ጥቂት ወታደር ይዞ ከፊቱ በመታየቱ ድፍረቱ እንዳስገረ
መው ፤ እንደነገሩት እውነትም ልጅና ዕውቀት የሌለው ቂል መሆኑን ፤ ነገር ግን
ኃላፊነቱ እውነተኛውን ነገር በሚያውቀው በሕዝቡ ላይ ቢደረግ ስሕተት መሆ
ኑን ሕዝቡ ግን የንጉሣቸው (የግራኝ) ታማኞች ባለመሆናቸው ይህ ነገር እንደሚያስ
ገርም ፤ ያች ሴት (ንግሥት ሰብለ ወንጌል) እንዳታለለችው አሁን ደህና አድርጎ እን
ዲያውቅና ለወደፊት እርሷን እንዳያስብ ፤ እርሱ ግን (ግራኝ) መሐሪ ንጉሥ በመ
ሆኑ እንደሚራራለት ፤ ከዚህ ቀደም ስላደረገው ድፍረት ግን እንደዚህ ያለ ነገር ፲፩
ዓመት በዚች አገር አግኝቶት ስለማያውቅ እርሱን በመቃወሙ ከፖርቱጋሎች
ሁሉ ጋር በፍጥነት ወደርሱ የመጣ እንደሆነ ለዚሁ ድፍረት ይቅርታ እንደሚያደር
ግለት ፤ ከርሱ ጋር አንድነት ለመሥራት ያልፈቀደ እንደሆነ ግን ወደ አገሩ እንዲ
መለስ ፤ ይኸንንም ቢያደርግ አንዳች ክፉት ነገር እንዳያገኘው እንደሚያረጋግጥ
ለት ፤ ስለዕድሜው ማነስና ዕውቀት ስለሌለው በዚያች መንግሥት (በኢትዮጵያ)
ከርሱ (ከግራኝ) በስተቀር ሌላ ንጉሥ አለ እያለች ሴቲቱ ከስሕተት እንዳደረሰችው
አረጋግጦ ስለሚያውቅ ትልቁን ቸርነቱን እንደሚያሳየው ፤ አሁን ግን እውነተኛ
ውን ነገር ስለአመለከተው ያዘዘውን መፈጸም እንዳለበት» ።

ኩሩውና ኃያሉ ግራኝ ይኸን ደብዳቤ በመላክ ለክርስቶፎሮስ ዱጋማና ከርሱ
ጋር ላሉት ፖርቱጊዞች ይኸን የመሰለ የምርጫ መንገድ በዛቻና በምሕረት መካ
ከል እያሳየ ከዚሁ ጋር ዛቻውን በመሳለቅ ለመግለጽ ሲል የመጡትን የፖርቱጋል
ተወላጆች ጉበዛዝት አይደላችሁም መነኩሴዎች ናችሁ ለማለት የመነኩሴ ቆብና

(1) መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 1 ቍጥር 9 - 10

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 13 ። Histoire du Christianisme ገጽ 114 - 116

ISIC

መቁጠሪያ በመላክ እንደ ዘበተባቸው በዚሁ ምዕራፍ ተጽፏል ። ከዚሁ አያይዞም ክርስቶፎሮስ የግራኝን መልክት ከሰማና ለመልክተኛው ትልቅ ክብርና ደግነት ከማሳየት ጋር የቀይ ሐር ኮትና ውድ የሆነ ኒሻን ያለበት ቀይ ቆብ እንደሸለመው የዚህን መልስ ለግራኝ ኋላ ስለሚልክ ወደ ሠፈሩ እንዲሄድ እንደ አሰናበተው መልክተኛውም ከሠፈሩ እስኪወጣ ድረስ እንዲሸኙት ማድረጉን ከዚህ በኋላ ለግራኝ ምን እንደሚለውና መልሱን ማን እንደሚወስድለት ከጦር አለቆቹና ከመኳንንቱ ጋር እንደተማከረ ፣ የግራኝን ሰዎች ለማመን ስለማይቻል ፣ የፖርቱጋል ሰው እንዳይላክ መስማማታቸውንና ከጦርነት ላይ የማረከው ያንድ ፖርቱጋል አገልጋይ ስለነበረ መልእክቱ በእርሱ እጅ እንዲላክ ስለተደረገ ፣ ወዲያው ጥሩ እንዲለብስና የሚቀመጥበት በቅሎ እንዲሰጠው ከተደረገ በኋላ ግራኝ እንዲያነበው በዓረብኛ በተጻፈ አጭር ቃላት እንደዚህ የሚል መጻፉን ያመለክታል ።

«በባሕር ላይ ትልቅ ጀግና በምድር ኃይለኛ ገዥ በሆነው ትእዛዝ ወደዚህ እንደመጣ ፣ አቅም ለሌላቸውና ርዳታውን ለሚፈልጉ ሰዎች መርዳት ምን ጊዜም ልማዱ እንደሆነ በጣም ክርስቲያን የሆነው ንጉሥ (1) የጦር ወንድሙ የኢትዮጵያ ንጉሥ በከሐዲዎችና በቅዱስ ካቶሊካዊ ሃይማኖታችን ጠላቶች እንደተጨነቀና አገሮቹን እንደተቀማ ስላወቀ እንደሚያየው የነዚህን ጥቂቶች ወታደሮች ርዳታ ላከለት ፤ [illegible] እንጂ እነርሱም ለነዚህ ለተበላሹና መጥፎ ሰዎች ደህና አድርገው መብቃታቸውን በበኩሉ ፍትሕና ቅንነት ስለሚገኝ እስላሞችን ለማጥፋት መብቃታቸውን ይህችን አገር እስላሞች መግዛታቸውም ኢትዮጵያውያን በሠሩት ኃጢአት ጌታ ሊቀጣቸው ስለፈለገ መሆኑን እንግዲህ ግን ነፃ እንዲሆኑና ወደነበራቸው ኃይል እንዲመለሱ ተስፋ ማድረጉን ፖርቱጋሎች ወደ እርሱ ወደ ግራኝ መምጣታቸውና በምን ምክንያት ከዚህ እንዳሉ በነጋታው እንደሚያሳዩት የሚታዘዙትን የሕንድ ነገሥታት ሁሉ የዓረብ አገር የፋርስና የሚበልጠው የአፍሪካ ክፍል እስከ ባሪ በሆነው በፖርቱጋል ንጉሥ ብቻ መሆኑን በጌታ ርዳታ እርሱንም (ግራኝን) እንዲሁ (ገባር) ለማድረግ እንደሚፈልግ» ።

ግራኝ መነኩሴዎች ናችሁ ላለው አጻፋውን ለመመለስ አንተም ሴት ነህ ለማለት አንድ ትንሽ የቅንድብ ማስተካከያ መቀስና አንድ በጣም ትልቅ መስተዋት ላከለት (2) ። ሁለቱ ኃያላን መሪዎች በዚህ ዓይነት የንቀት ደብዳቤና የመሳለቂያ መሣሪያ ከተለዋወጡ በኋላ የጥይት ተኩስ የሰይፍ በትር በመለዋወጥ ያደረጉትን ውጊያ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ እንመልከት ።

(1) የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ ማለት ነው ።
(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት በነአቶ ዮና ትርጉም ምዕራፍ 13

## ምዕራፍ ፻፲፮

## ፖርቱጋሎችና ኢትዮጵያውያን ከግራኝ ጋር በሰሀርት (እንደርታ) ተዋግተው እን ዳሸነፉ (፲፭፻፴፩ ዓ. ም. መጋቢት ፳፱ ቀን)

ባለፈው ባዔ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ባደረገው ጦርነት ሁሉ ግራኝ አህመድ የክርስቲያኖቹን የጦር አለቆች አብዛኛ ጊዜ ማሸነፍ የቻለው በተንኮልና በዘዴ አደጋ እየጣለ ለየብቻ እየለየ ፊት ለፊትም በመዋጋት ነው ። ባንድነት ያበረውን ጠላት በድምሩ ዝም ብሎ በመውጋት ፈንታ እየሸሸም ቢሆን ጊዜና ሥፍራ እያማረጡ አደጋ እየጣሉ ጠላትን እየለያዩ መውጋት ለድል አድራጊነት ዓይነተኛ ጥቅም መሆኑ ምን ጊዜም በየጦርነቱ ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ የታየና በጽሑፍም ሠፍሮ ብዙ ጊዜ የሚነበብ ነው ። ይኸም በሁለት ተዋጊ በኩል የማይሳት ቢሆንም በዚህ ዘዴ ለመጠቀም የሚችለው በሥፍራ አመራረጥና በአወጋግ ዘዴ ይበልጥ ዘዴኛ የሆነው መሪ ነው ።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ግራኝ አህመድ በታማኞቹና በሰላዮቹ አማካይነት ዓፄ ገላውዴዎስ ከነሰዋቸው ባንድ ወገን ፤ ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ፖርቱጋሎቹ በሌላ ወገን ያሉበትን የተራራቀ ሥፍራ በትክክል ስለሚያውቅ ከሸዋ ናስር አድ ዲንን አሸንፈው ከማርቆስ ጋር ወደ ስሜን የተመለሱትን ዓፄ ገላውዴዎስን ተከታትሎ በማጥቃት ፈንታ ምንም በደብዳቤው የንቀት ISIC ምልክ ቢያሳይ አዳዲስ የጦር መሣሪያና መድፍ ይዘው መጥተው በንግሥቲቱ ዙሪያ ተሰብስበዋል ፤ የባሕር ነጋሹ ጦር አብሯቸው አለ ያንተ ተገዥ የነበረው የአጋሜ የእንደርታ ሕዝብም ለነሱ ገብቷል እያሉ የነገሩትን ለማጥፋት ሳይታሰብ ከደረሰኄ "ስሜን" ወደ ሰሀርት (እንደርታ) መጥቷል ማለት ነው ። ለመኖሪያ ከመረጠው ከለምለሙ አገር ከደምቢያ ወደ ደረስጌ የተዛወረው ዓፄ ገላውዴዎስን ፍለጋ ሳይሆን አይቀርም ። ግራኝ አህመድ ከክርስቶፎሮስ ጋር ጦርነቱን ከመግጠሙ በፊት ከልቡ ይሁን ወይም ከአፉ በማስፈራራት ወይም የመጡበትን መሠረታዊ ዓላማ ትተው ወደርሱ እንዲዞሩ ይኸም የማይሆንላቸው ቢሆን የተከተሏቸውን ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ከድተው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደሚታየው ጽሑፉ የምርጫ መንገድ የሚሰጥ ቢሆንም ለመሳለቂያ የላከው የመነኵሴ ቆብና መቁጠሪያ እንደ ክርስቶፎሮስ ላለ ዠግና መኰንን ስድብ ስለሆነ ለዚሁ አጸፋ ደጋግም በበኩሉ የስድብ ቃልና የመሳለቂያውን መሣሪያ መስተዋትና መቀስ ከላከ ወዲህ ለውጊያው ዝግጅት አድርጓል ።

ያገራችን ታሪክ ነገሥት ባለፈው ያነበብነውን የፈረንጆቹን አመጣጥ "ጦርነት እንደ ተኩላ የጠማቸው እንደ አንበሳ የራባቸው የያፌት ልጅ የቶቤል ልጆች ከባሕር መጡ" በሚል አነጋገር ከገለጠና «ግራኝ በደረስጌ ከርሞ ከዚያ በታኅሣሥ ወር ወደ ትግሬ ሄደ ። ፈረንጆቹ በምክርና በዘዴ ከምታበረታቸው ገንዘብ እየሰጠች ምግብ ከምትመግባቸው ከንጉሡ እናት ከሰብለ ወንጌል ጋር ነበሩ» ካለ በኋላ አሁን ደግሞ ከዚያው አከታትሎ «በእነሂ በመጋቢት ፳፱ ቀን ተዋግተው ግራኝ

በጥይት ተመታ ። ነገር ግን አልሞተም» ሲል የሰጠውን አጭር አተራረክ (1) ካስታንሆዞ የጻፈው እነ አቶ ዮና ቦጋለ የተረጐሙት መጽሐፍ በደንብ እየዘረዘረ እንደዚህ ሲል ያመጣዋል ።

«. . . . . መድፎቹን ከሠረገላዎቹ ድንኳኖቹንና ዕቃዎቹን ከበቅሎች ላይ ከጫንን በኋላ ዶም ክርስቶፎሮስ ሰዎቹን ለውጊያ ያሰልፋቸው ዠመር . . . ወገግ ብሎ ሲነጋ ማክሰኞ ሚያዝያ ፬ ቀን ፲፭፻፵፪ (መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፭፻፴፬ ዓ. ም.) ጠላትን ለመግጠም ጉዞ ዠመርን ። በዚህም ጊዜ ዶም ክርስቶፎሮስ ከስምንት የፖርቱጋል ፈረሰኞችና ከአራት እስከ አምስት ከሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ጋር (ታጅቦ) በፈረስ ወደ ሠራዊቱ እየሄደ ሰዎቹን (ተዋጊውን) ያዘጋጅ ነበር ። ልንገጥማቸው መሄዳችንን ዓረቦቹ ባዩ ጊዜ ዓለም እንደ ጠፋች በጥሩምባና በነጋሪት ድምፅ ትልቅ ፉከራ ተነሣ (አስነሱ) ። ከወጥመዱ (ከወጥመዳቸው) ገብተን ያገኙን ስለመሰላቸው ባጣም ደስ ብሏቸው ነበር ። በዚያን ጊዜ በመድፍና በጠበንጃ ሥራችንን ዠመርን . . . . . . ግንባር ቀደም የሆኑት ቱርኮች ያደረግነውን ጉዳት በተመለከቱ ጊዜ በጣም ወደኛ ቀረቡ ። ከዚህ ላይ እጅግ ኃይለኛ የሆነ ጦርነት ተነሣ ። ዋናው ምርኩዞች (ጸንተው የሚዋጉት) ቱርኮች መሆናቸውን በተመለከተ ጊዜ ግራኝ ከአምስት መቶ ፈረሰኞች ጋር . . . . . ወደኛ ያመራ ጀመር ።

የዚያን ፲፭፻፵፪ ከትልቅ ጭንቀት ገባን ። ግን መድፈኞቻችንን የያዙት ወታደሮች እንደ ጀግኖች (በዠግንነት) ያለ ፍርሃት . . . . . ቶሎ ቶሎ ስለተኮሱባቸው ፈረሶቹ እየፈሩ (ስላፈገፈጉ) የጠላትን ፈረሰኞች እንዳይቀርቡ አደረጉዋቸው ። ቢሆንም የግራኝ ሠራዊት ይልቁንም ቱርኮቹ በጠበንጃዎቻቸው ብዙ ጉዳት አደረጉብን ። ዶም ክርስቶፎሮስ ይኸን ባየ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ውጊያውን ለጊዜው እንዲተውትና መድፈኞች ብቻ እንዲዋጉ አደረገ ። በዚህም ትልቅ ጉዳት አደረግንባቸው ።

መቶ ቱርኮች በጣም የቀረቡን ጊዜ ዳ. ኩንሃን አምሳ ከሚሆኑ ሰዎቹ . . . . ጋር ሆኖ እንዲገጥማቸው አዘዘው . . . . . . ቱርኮቹም ወደ ሰንደቅ ዓላማው ቀርበው ሰንደቅ ዓላማ ተሸካሚውንና ሦስት ፖርቱጋሎች ገደሉ . . . . . . የኛዎቹም ከቱርኮቹ ውስጥ ገድለዋል ። ዳ ኩንሃን ቀኝ እግሩን በጠበንጃ ጥይት ስለቆሰለ ከጦርነቱ ማሀል መውጣት ግዴታ ሆነበት . . . . . . ዶም ክርስቶፎሮስም ከአደገኛው ቦታ እየገባ በመዋጋት ወታደሩን ያደፋፍር ነበር . . . . . . ይኸን ሲያደርግ እግሩን . . . . . . በጥይት ቆሰለ . . . . . . ጦርነቱ በዚህ ዓይነት ሆኖ . . . . . . ድል ሆንን ብለን ስናስብ በውጭ ሆኖ ይመለከት የነበረው ግራኝ . . . . . . ሰዎቹን ለማደፋፈር . . . . . . በጣም ስለቀረበን ባንድ የጠበንጃ ጥይት ጭኑን ቆሰለ ፈረሱ ግን እንደኛውን ተበላሽቶ ስለነበረ ሞቶ ግራኝን እንደያዘው ወደቀ ። ሰንደቅ ዓላማ ተሸካሚዎቹ ሲወድቅ ባዩት ጊዜ ሦስቱን ሰንደቅ ዓላማዎቻቸውን ዝቅ

(1) . . . . . እፍርንጅኒ ወጽኡ እምደባርዋ እንዘ ምስሌሆሙ ይቱ (አቴኔ) ሰብለ ወንጌል እሙ ንጉሥ ወታስተጻንዖሙ በጥበብ ወምክር ወትሜግቦሙ በሲሳይ . . . . . ወተራከቡ ምስለ ግራኝ በምድረ እንጻ ወገብሩ ፀብአ በሕየ አመ ፳ወ፱ ለመጋቢት ወነደፍዎ በነፍጥ ወኢሞተ . . . . . ታሪክ ነገሥት ሬ ባሴት ያሳተሙው ገጽ 330



ክርስቶፎሮስ ዳጋማ ከጭፍሮቹ ጋር ሆኖ እስላሞቹን ሲያባርር (ከሜረር)

አደረጉ ። ይኸም በርሱ ዘንድ የመመለስ ምልክት ስለነበረ . . . . . ወዲያው (ግራኝን) በክንዳቸው ላይ ተሸከመው በፍጥነት ይዘውት ሄዱ ።

ዶም ክርስቶፎሮስ ይኸንኑ ባየ ጊዜ ግራኝ እንደቆሰለ ተመለከተና ጥሩምባዎች እንዲነፉ ነጋሪቶችም እንዲመቱ አደረገ ። እኛና ከኛ ጋር የነበሩት ሁለት መቶ ኢትዮጵያውያን ባነርሱ ፎክረን ገባንባቸው ። ከነርሱም ብዙዎችን ገደልን . . . . . ከዚህም ላይ ኢትዮጵያውያኑ እንደ በግ እያረዱ በግራኝ ሠራዊት ላይ ተበቀሉ ፣ እነርሱን ለመከታተል የበቃ የፈረሰኛ ጦር አለመኖሩንና እኛም በጣም መድከማችንን ዶም ክርስቶፎሮስ ባየ ጊዜ ደግሞም የግራኝ ፈረሰኞች እንዳይመለሱ ስለፈራ በዚሁ ቀን ጌታ በሰጠው ድል ደስ እንዲለው አደረገ ።

እኛ ስንከታተላቸው (የግራኝን ጦር) ንግሥቲቱ አንድ ድንኳን አስተክላ ቁስለኞችን አስገባች ። እርስዋ ራስዋና ደንገጡሮቿ በየራሳቸው ራስ መሸፈኛ (ሻሽ ማሠሪያ ወይም ቀጸላ) ቁስላቸውን ያሥሩላቸው ነበር ። በእውነት በጣም ፊርታና አዝና ስለነበር በዚሁ ቀን ጌታ ስላደረገላት ትልቅ ቸርነት በደስታ ታለቅስ ነበር . . . . . .» (1) ።

ጦርነቱን የተካፈለውና በውጊያ የቆሰለው ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ የጦርነቱን ሁኔታ በዚህ ዓይነት ከዚህም ሰፋ አድርጎ ከጻፈ በኋላ በጦርነቱ ሜዳ የወደቁት የፖርቱጋሎች ቍጥር ፲፩ እንደነበሩና ከነዚሁ መካከል ሉዊዝ ሮድሪጌዝ ዴ ካርቫልሆ ፤ ሎፖ ዳ ኩንሃ የሚባሉት ሹማምንት መሞታቸውን በጠበንጃ የቆሰሉት ቁጥራቸው ከሃምሳ መብለጡን የጠላት ሬሳ ግን በብዛት ሜዳውን ሸፍኖት እንደነበረ ከነርሱም ውስጥ አራቱ የግራኝ ዋና የጦር አዛዦች መሆናቸውን ኢትዮጵያውያኑ ዓይተው እንዳወቋቸው የሞቱት የቱርኮች ቍጥር በሜዳ ላይ ሬሳቸው የተገኘው አርባ መሆኑን ያረጋግጣል ።

እዚህ ላይ ደ ካስታንሆዞ በጣም ዋጋ የሚሰጠው ለራሱ ወገኖች ለፖርቱጋሎችና ከግራኝም ወገን ለቱርኮቹ ስለሆነ ከወዲህም ከወዲያም የሞቱትን ቁጥር የቱርኮቹንና የፖርቱጋሎቹን ሲጽፍ የኢትዮጵያውያኑን የክርስቲያኖችና የእስላሞቹን ቍጥር አይናገርም ። ከብዛታቸውም የተነሣ መቁጠሩ አሰልችቶት ይሁን ወይም አዳዲስ ጠበንጃ ያልያዙትን በዘመናዊ ትጥቅ ያልሠለጠኑትን ባለጦርና ባለ ሰይፍ ድምር ሕዝብ በመናቅ ይሁን በትክክል አይታወቅም ።

የሆነ ሆኖ እነሆ ግራኝ እንዚሁ ቍጥራቸው ያነሰ መንኰሳት እያለ ቆብና መቁጠሪያ በመላክ የናቃቸው ወታደሮች በጥይት አቁስለው በመጣል እዚሁ ላይ አደረሱት ። ቀድሞ በሽምብራ ኩሬ በርሱ አሸናፊነት ሟቹ ዓፄ ልብነ ድንግል እንደተገረሙ የሰውነት ስም መስጠትም ጠልተው "በሰው የተመሰለው ሰይጣን" ይሉት እንደነበረው እርሱም ባሁኑ ሰዓት ቆስሎ የሳንሳ ይዘውት ወገኖቹ ሲሸሹ የቀድሞ አሸናፊነቱን ከማሰብ ጋር አሁን በነዚህ በናቃቸው ሰዎች መሸነፉ ነገሩ ሳይገርመው አይቀርም ።

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 10

በ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. በደዋሮ ራስ ደገልሃንን ካሸነፈ ዠምሮ እስከዚህ እስከ ፲፭፻ ፴፩ ዓ. ም. ድረስ በአሥራ አምስት ዓመት ውስጥ ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን ማባረርን እንጂ መሸሽን የማያውቀው ግራኝ አህመድ በዚያ ሁሉ ዘዶውና ተንኰሉ መካከል እነሆ ለመዠመሪያ ጊዜ ከጦር ሜዳ ላይ ቆስሎ ወገኖቹ ይዘውት ሲሸሹ ታየ ። ባይቆስል ኖሮም ቢሆን የጦርነቱ ዕድል ሲያጋድልበት እየተዋጋ ከመሞት ወይም ከመማረክ የትኛውን ይመርጥ እንደነበረ አይታወቅም ። የሆነ ሆኖ እዚህ ላይ የድል አብነት ከጦርጦራ መሪ ጋር የጦር መሣሪያ በተለይ ጠበንጃ መሆኑን በትክክል እንረዳለን ።

የሆነ ሆኖ ለግራኝ አህመድ ባላጋራ ሆኖ የጦር አመራሩን ሊይዝ የሚገባው እንደዚህ ያለው ወጣትነት ያለው የንጉሥነት ማዕርግ የዘውድ ክብር የማይጫነው ወዲያና ወዲህ በፈረስ እየተራወጠ የአወጋግ ዘዴ በአላፊነት እየፈጠረ ራሱ እየተዋጋ ወታደሩን የሚያዋጋ ጦርጦራ መሪ እንጂ የዓፄ ልብነ ድንግል ዓይነት ባለዘውድና ወግ ማዕርግ የሚጫነው አለመሆኑን ከዚህ በፊት ያወሳነው በዚህ ጦርነት ላይ በክርስቶፎሮስና በግራኝ መካከል ይታያል ። ግራኝ አህመድ ከ፲፭ ዓመት በፊት የ፳፩ ዓመት ወጣትና አፍላ በነበረበት ሰዓት ጦሩን እየመራ ያዋጋ የነበረው እንደ ዚህ እንደ ክርስቶፎሮስ ዶጋማ ወጣት በነበረበት ሰዓት ነው ። እንደ ክርስቶፎሮስ እንሸሽ ወይም ጦርነቱ ውሎ ይደር ብሎ ምክር የሚያቀርብለትን የማይወድ ድካም የማይሰማው ድልና ምርኮ የማይበ[illegible]ው ደፋር መሪ እንደነበረ ያለፉት ምዕራፎች ሁሉ አስገንዝበውናል ።

ባሁኑ ጦርነት ዋዜማ እንኳ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፖርቱጋሎቹ ጋር ተዋግቶ ኃይላቸውን አመዛዝኖ ስለነበረ ፖርቱጋሎች በአፋቸው እሳት የሚተፉ ናቸውና በዚህ ሥፍራ ባንዋጋ ይሻላል ብሎ ግራኝን ቢመክረው «ተራራ አይሸሽም» ብሎ ምክሩን ሳይሰማ እንደተዋጋና ከመቁሰል እንደደረሰ በኋላ ደግሞ በሸሸት ጊዜ ይኸው እንኳ «ተራራ ይሸሻልን ?» ብሎ ቢጠይቀው «ተራራም ወደ እሳት መጠጋት አይችልም» ብሎ እንደመለሰለት ዠሮም ሎቦ የሚባለው ሚሲዮናዊ በጻፈው ማስታወሻና ለግራን ወደ ፈረንሳዊ በተረጐመው ላይ ይነበባል (1) ። ይኸም ግራኝ አህመድ ባለፈው ድል አድራጊነቱ ተመክቶ ንቀት ባለበት መንፈስ መዋጋቱን ያስረዳል ።

በዚህም ላይ አሁን ዕድሜው ከ፴፮ ዓመት ላይ ገብቶ የገዥነት ኩራት በኑሮውም ተድላና ደስታም ተጫጭኖት ይሆናል ። ከቅምጥልነትና ከጌትነት ዘወትር ከማሸነፍ የተነሣ ምናልባትም ድል አድራጊነት የሰለቸውና ጠላቶቹን የናቀው ግራኝ አሁን እነሆ በወጣቱና ድል በጠማው በክርስቶፎሮስ ፊት መቆም አልቻለም ። በተዋጊዎቹ ባላጋራዎች በሁለቱም ወገን መድፍና ጠበንጃ አለ ። በነዚህ ወገን ፖርቱጋሎች ሲኖሩ በነዚያም ውስጥ እነዚያ በኃይል የተዋጉት ቱርኮች አሉ ። ምናልባት በመሣሪያ ጥራት የፖርቱጋሎቹ ትንሽ ቢበልጥም በጦር ሠራ

(1) Voyage Historique-J.LOBO ገጽ 90 - 93

ዊት ብዛት ግራኝ ሳይካስ አልቀረም ።

ነገር ግን ጦርነቱ በሁለቱም በኩል ተፋፍም ሲቀጥል ምናልባት ሁለቱ በሞትና በሕይወት መካከል በመጨረሻ ኃይላቸው ሲጠቀሙ የግራኝ ከፉኛ ተመ ትቶ መውደቅ ለፖርቱጋሎችና ለኢትዮጵያውያኑ አጋጣሚ ድል ሆኖላቸዋል ማለት ነው ።

የዚህ ቀን ጦርነት ታሪክ በዚህ ዓይነት ተዠምሮ መፈጸሙን ደ ካስታንሆዞ ሲያመለክተን በበኩሉ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ የሌለ አንዳ ንድ ዝርዝር ነገር በማምጣት ይተርካል ። በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ ግራኝ ያሰ ተለው ጦር ፱፻ የቱርክ ነፍጠኞች ፣ ፩ሺ፭፻ ፈረሰኛ ፲፭ሺ እግረኛ "ጦረኛና ቀለ ተኛ" ሲሆን የቤርሙዴዝ መጽሐፍ ከዚህ ዝቅ አድርጎ ፩ሺ ፈረሰኛ ፣ ፭ሺ እግረኛ ፱ የቱርክ ነፍጠኛ "MOUSQUETAIRES" ያደርገዋል (1) ።

ነገር ግን ያገሩ ጌታ ለሆነው ለግራኝ ከአዳልና ከሐረርጌ ተከትሎት የመጣው በአሁኑ ሰዓት በውድም በግድም የሚከተለው ያገር ተወላጅ ሁሉ ሲታሰብ ምንም እንኳን ቤርሙዴዝ ያለውን ለመጥቀስ ያህል ብናወሳውም የሚመስለውና ትክ ኛው የካስታንሆዞ አጻጻፍ ነው ማለት ይቻላል ።

ከዚህ አያይዞ "ጦርነቱ ሊዠመር ሲል ክርስቶፎሮስ ደጋማ ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ከነጓዟ በተዋጊው መካከል አሥፍሯት በነበረ ጊዜ በጣም ፍርሃት አደሮ ባት ነበር ። አቅራቢያችን ወደሚገኘው የርጎራጌ እመቤት (ማርያም ?) ቤተ ክርስ ቲያን ወዳለበት ጉብታ ስናቀና የጠላት ጦር ዞሮ አገደን ። ከዚያ በኋላ ውጊያ ተዠ ምሮ ሁለቱ ወገኖች ሲታኰሱ ስድስት የፖርቱጋል ወታደሮች ጠርቼ እኔና ንግሥ ቲቱ ከነእህቶቿ ከጦርነቱ ቦታ ለየት ብለን ባለንበት ቦታ ሳለን የሞሩን ንጉሥ "ግራኝ አህመድን" በፈረሱ ላይ ሆኖ በባንዲራው አጠገብ ሆኖ ስላየሁት ጴየርስ ደቻ (Pierre Deça) ለሚባለው ወታደራችን ያውልህ ብዬ አመልክቼው የተኰ ሰው ጥይት ፈረሱን ገድሎ ቅልጥሙን አቆሰለው" ይላል ።

እዚህ ላይ ስለ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ፍርሃት የተናገረው ከሴትነታቸው በቀር በግራኝ እጅ መማረክን ስለሚሰቀቁ አልፈሩም ወይም አይፈሩም ማለት አይ ቻልም ። እንኳን ርሳቸው ሴቷ እርሱ ወንዱም መፍራቱ የማይጠረጠር ሆኖ ባለ የራሱን ፍርሃት አልጠቀሰውም ። ወይም የርሱን ፍርሃት በርሳቸው ሸፍኖታል ።

በርሱ አመልካችነት የግራኝን መቁሰል የጻፈው ምንም እንኳን በካስታንሆዞ መጽሐፍ አቁሳዩ ባይወሳ ሊሆን የሚችል ነገር ነው ። ወደ ሊስቦን ከመሄዱ በፊት እንደ አው. ቍጥር ከ፲፭፻፳ እስከ ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ድረስ ፲፩ ዓመት በኢትዮጵያ ስለተቀመጠ በጦርነቱም ሰዓት ከ፲፭፻፳፮ እስከ ሄደበት ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ድረስ ዘጠኝ ዓመት ያህል የጦርነቱን መከራ ባዬ ልብነ ድንግል አጠገብ ሆኖ ስለተካፈለ የዋስል ጦርነት ለት ንጉሡ ግራኝን በግራ እጁ እየተማታ ሲዋጋ ዓይተው «በሰው የተመሰለው ሰይጣን ያውና» ያሉ ለት እርሱም አብሮ በማየት አውቆት ባሁኑ ጊዜ

(1) Histoire du Christianisme . . . . . . ገጽ 116

ተመልክቶ አስተኩሶበት ይሆናልና ሊያከራክር አይችልም ። ቤርሙዴዝ ከዚሁ በማያያዝ « ከዚህ ድል በኋላ የባሕር ነጋሹ (ይስሐቅ) የቅርብ ዘመድ ( Cousin germain ) የዚህ አውራጃ ገዥ ሆኖ በከዳተኝነት ግራኝን ያገለግል የነበረው ሹም ወደኛ መጥቶ የግራኝን የአቀሳሰሉን ወሬ ነገረን ባይቀስልና ባይመለስም ኖሮ ሁላችንም አላቂዎች እንደነበርን አስረድቶ ለወደፊቱ ዋና አገልጋያችን እንደሚሆን ለግራኝ የሚሰጠውን ያገር ግብር ለኛ እንደሚገብር አረጋግጦ ገባ» ይላል (1)።

ጦርነቱ የተደረገበትን ቦታ ግዕዙ በተለይ ምድረ አነፃ "ያለውን ካስታንሆዞ የያርት ሜዳ ብሎታል ። እርሱም የውጭ አገር ሰው በመሆኑ አጠራሩ ባይገባው ነው እንጂ የሰሀርት ሜዳ ማለቱ ይመስላል ። በግዕዝኛው አጠራር አነፃ የሚል ቀበሌ በዛሬ ጊዜ መኖሩን አላረጋገጥም ። በዛሬው የግዛት ድልድል ይህ ጦርነት የተደረገበት አገር አውራጃው እንደርታ ወረዳው ስሀርት ከተማው ግጀት ይባላል ።

የሆነ ሆኖ እዚህ ላይ አንባቢ ሊገነዘብ የሚገባው ከዚህ በፊት በ፲፭፻፳፱ ዓ.ም. በግራኝና በራስ ነቢያት መካከል በተደረገው ውጊያ ሁስማን የተባለው በተኩሳት ባንዲት የነፍጥ ጥይት እነራስ ነቢያትን አስበርግጎ እንዳሸሸና ጦሩን እንደፈታ እሁ ንም ይህ ከፍ ያለው በግራኝ የጦር ግንባር ያለው ጦር ለመፈታት የቻለው ግራኝ ሊቆስልበት በቻለው ባንዲት ጥይት ምክንያት ነው (2) ። ከዠግና ተዋጊ ቆርጦ ከልቡ ከተነሣ ብልህ መሪ ጋር የመሣሪያ ጥራት የድል አብነት መሆኑን እዚህ ላይ በድጋሚ እንመለከታለን ። ISIC

ምዕራፍ ፻፲፰

ክርስቶፎሮስ ደጋግሞ ግራኝን እያባረረ ለመውጋት ሳይሳካለት እንደቀረና ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ወደ አሸንጌ ሐይቅ እንደሄዱ (፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ሚያዝያ - ነሐሴ)

በዚህ በመጋቢት ፳፱ ቀን ይኸን ድል ካገኙ በኋላ ምንም ቁስለኛ ቢበረከት ስለ ሞቱት ኢትዮጵያውያንና ፖርቱጊዞችም ኀዘን ባይቀር ስለተገኘው ድል ታላቅ ደስታ ሆኖ የፋሲካን በዓል ሁሉም እንደልማዳቸው አክብረው ዋሉ ። የድሉ ሁኔታ በንግሥት ሰብለ ወንጌል ዘንድ የፈጠረውን የደስታ መንፈስ ከገለጠበት ላይ "በደ ስታ ብዛት ታለቅስ ነበር" ሲል ካስታንሆዞ ያወሳው ትክክለኛ መሆን አለበት ። አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ያዘነ ሰውነታቸው በዚህ ቀን ተደስቷል ። ምናልባት በዚህ ጊዜ የሚያሳዝናቸው ከዚህ በፊት እንዳልነው ባለቤታቸው ዓፄ ልብነ ድን ግል ይኸን ግራኝ ቆስሎ የሸሸበትን የምሥራች ቀን ሳያዩና ሳይሰሙ ካመት በፊት መሞታቸው ይሆናል ።

ክርስቶፎሮስ በአምባ ሠንይት እንዳደረገው የዚህን ቀን ድል የግራኝን ቆስሎ

(1) Histoire du Christianisme ገጽ 117 - 119

(2) ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 144 - 145

መሸሽ ሌትና ቀን ገሥግሠው ምጥዋ ላሉት ፖርቱጊዞች እንዲነግሩና እነዚያም ወደ ሕንድ ላገረ ገዥው እንዲያደርሱ በምሥጢር ከላኩና ጭማሪ ርዳታም እንዲ ያገኝ አስቦ ለጊዜው ሳይደርስለት ስለቀረ በዚህ መካከል አሁን ቆስሎ የሸሸው ግራኝ አህመድ በመላ ኢትዮጵያ በየአውራጃው ብዙ ጦር አለውና ያንን እስኪሰበ ስብ ጊዜ መስጠት አይገባምና እንከታተለው ተብሎ ስለተወሰነ የፋሲካን በዓል በአከበሩበት ሳምንት በዳግማዊ ትንሣኤ ጦሩን አሰልፎ መድፎቹን አስጭኖ ግራ ኝና ጦሩ ወደ ሸሹበት አመራ ። በዚህም ጊዜ የግራኝ ሰዎች ቁስለኛውን ባሊጋ ቃሬዛ ይዘው ሲጓዙ ተያዩ (1) ። ለግራኝም ገራድ ኡመር የሚባለው አዲስ ጦር ይዞ ደርሶ ኖሮ በመዠመሪያ ባዲስ ጉልበት ጦርነቱን ከፍቶ ውጊያ ዠመረ ። ጦር ነቱ በሚጋጋልበትም ሰዓት የቀሩት ፈረሰኞች ከመድፉ ጩኸት የተነሣ መቃረብ ሳይችሉ ቢቀሩም ኡመር ራሱ ከአምስት ጓደኞቹ ጋር ወደፊት አልፎ ከፖርቱጋ ሎቹ ጋር በደፋርነት ሲዋጋ ሞተ ።

በዚህ ጦርነት በፖርቱጋሎቹ መካከል የነበረ ባሩድ በድንገት ፈንድቶ ሁለት ፖርቱጋሎች ሲገድል ስምንት ማቁሰሉን በጩኸቱም የእስላሞቹ ፈረሶች በድን ጋጤ ደንብረው ጌቶቻቸውን እንደያዙ ስለሸሹ ፖርቱጋሎቹ በፈረስ እጐዳ እንዳጣ ለን ብለው የነበራቸው ሥጋት እንደተወገደላቸው የፖርቱጋል እግረኞችና ፈረሰ ኞችም ተባብረው በአስደናቂ ዠግንነት ውጊያውን ስለቀጠሉ አሁንም የግራኝ ጦር መሸሹን ካስታኖሆ ያመለክታል ። ከዚህም አያይዞ እስላሞቹ ከጦርነቱ ቦታ በሚሸሹበት ጊዜ እያባረሩ ለመግደያ ፩፻ ፈረሶች ቢገኙ ኖሮ ዋናው ጦርነት በዚህ ቀን ተፈጽሞ አገሪቱ ነፃ በሆነች ነበር እያለ ከማረጋገጥ ጋር እስላሞቹን ደጋግ መው እየተከታተሉ በሚያባርሩበት ጊዜ ግራኝ አህመድ እንደ ቀልድ "እነዚህ መነኰሳት እረፍትም አልሰጡን" ብሎ የመናገሩን ወሬ አንድ ሰው እንዳመጣለት ይገልጻል ።

በዚህ ዓይነት ግራኝ አህመድ ቆብና መቁጠሪያ ልኮ መነኰሳት ናችሁ ብሎ የተሳለቀባቸውን የፖርቱጋል ወታደሮች በዚህ አነጋገር ዠግንነታቸውን ተረድቶ ላቸዋል ማለት ነው ። ሥፍራ እንለውጥ ብሎ ለመከረው እጐቱ "እንዴት ተራራ ይሸሻልን" ብሎ በመናገር በራሱ ጉልበት በፍጹም ተማምኖ የነበረው ሰውዬ ባሁኑ ጊዜ የራሱን ሰብአዊ ደካማነት በዚሁ በሽሽቱ ጊዜ በቃሬዛው አሊጋ ወይም በፈ ረሱ ላይ እንዳለ እንደሚገነዘበው የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፖርቱጋሎቹ ማባረር ደክሟቸው ወደ ኋላ ተመልሰው የሞተውና የቆሰለው ሲቆጠር በዚህ ቀን ጦርነት ፲፩ ፖርቱጋሎች ሞተው ፷ የሚሆኑ ቆስለው እንደነበረ ባወሳበት ምዕራፍ ላይ አንድ በጣም ዝግና የሆነ ኢትዮጵያዊ የጦር

(1) ካስታንሆሶ በዚህ ዓይነት የተረከውን ጀምስ ብሩስ ለየት አድርጎ ግራኝ ሰዎቹን ለማደፋፈር ከፊት ቀድሞ ሳለ በአለባበሱ ስለታወቀ ጴጥሮስ ደሳ እነጣጥሮ የተኰሳት ጥይት ፈረሱን ገድላ እርሱን ቅልጥሙን እንዳቆሰለች ግራኝም በቃሬዛ ሳይሆን በሌላ ፈረስ ተቀምጦ መሸሹን ያመለ ክታል ( ብሩስ በካስቲራ ትርጉም ፪ኛ ቮሊም ገጽ 198 ይኸንንም የጻፈው ከቤርሙዴዝ ጽሑፍ ላይ ገልብጦ ሳይሆን አይቀርም ።

አሊቃ አብር መሞቱን ሲገልጥ ስሙንና የግዛቱን ስም ስለማይናገር በጠቅላላው ከኢትዮጵያውያን ወገን የሞቱትንም የቆሰሉትንም ቁጥር ስለማይገልጽ በዚህ ጦር ነት የኢትዮጵያውያኑን የውጊያ ክፍያ እስከምን ድረስ መሆኑን ለማመዛዘን አል ቻልንም ። ለአገራቸውና ለሃይማኖታቸው ሲሉ በንግሥታቸው ዙሪያ የተሰበሰቡት የቆየ ደመኛ ጠላታቸውን ለመበቀል ታጥቀው የተነሡት ቀድሞውኑ ትጥቃቸውን ካልፈቱት ጋር ብዙ እንደሚሆኑ ፤ ብዙዎቹም በዚህ ቀን ጦርነት ሕይወታቸውን የሰጡ እንደሚገኙባቸው የታወቀ ነው ። ዓረብ ፋቂህ እስከ ግራኝ ሞት ድረስ ታሪ ኩን ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ የርሱ ጽሑፍ ከካስታንሆዞ ጋር የተሟላ ሆኖ ዝርዝር ሁኔታ ውን ከሁለቱም ወገን ለመረዳት በተቻለ ነበር ። ካስታንሆዞ ባንድ ወገን እየተዋጋ ባንድ ወገን ይኸን ማስታወሻ ሲጽፍ በዚህ ላይ ያለበትን አገር ቋንቋ የማያውቅ እን ግዳ ስለሆነ በውጊያው ጊዜ የወታደርና የሹማምንት ቁጥር የሰውና የአገር ስም መጠየቁና መመራመሩ ችግር ይሆንበታል ። የክፍላቸውን ታሪክ በዝርዝር መጻፍ የነበረባቸው የኛዎቹ ነበሩ ። እነርሱም ባለፈው እንደተመለከትነው ገድልና ድር ሳን ሌላም መንፈሳዊ ጽሑፍ አበርክተው በሚጽፉበት መጠን በጠቅላላው ለሥነ ጽሑፍ ወይም ለዝርዝር ታሪካዊ ጽሑፍ አጥብቀ ካለማሰብ የተነሣ ጉዳዩን ባጭሩ ቀንጨብ አድርጎ ከማለፍ በቀር በዝርዝር እንደ ዓረብ ፋቂህ ያም ቢቀር እንደ እንግዳው እንደ ካስታንሆዞ መጻፍ ስላልቻሉና ወደ ጊዜያችን ስለአላስተላለፉልን የብዙ ወገኖቻችን አርበኝነትና ዠግንነት የብዙ አለቆች ሰማዕትነት እንደዚሁ ተደ ፍና መቅረቱ ያሳዝናል ።

ካስታንሆዞ ይኸን ማስታወሻ ባይተውልንም ኖሮ ዓረብ ፋቂህም ሞቶ ይሁን ወይም አገሩ ገብቶ በዚህ ጊዜ ስለሌለ እነሆ ምጥዋ ከደረሱበት ቀን ዠምሮ እስከ ግራኝ ሞት ድረስ ፖርቱጋሎቹና ኢትዮጵያውያኑ በኅብረት ያደረጉት ይህ ታሪ ካዊ ጦርነት እንደተደፈነ ይቀር ነበር ማለት ነው ። በአጻጻፍ ግን እንደምንመለከ ተው ከካስታንሆዞ ዓረብ ፋቂህ ይበልጣል ። በታሪኩ ውስጥ ስናነብ እንደተረዳነው ሰውዬው እንደተወላጅ ለጉዳዩና ለአገሩ ለቋንቋውም ቀረብ ከማለቱና የኢትዮ ጵያና የዓረብ ሕዝብ ከአላቸው ቤተ ሰብነት የተነሣ የቦታ ስም ከሁለቱም ወገን ያሉትን የተዋጊዎቹን የሹመትና የመጠሪያ ስም ይነስ ይብዛ በደንብ እየለየ የጻፈ ውን እናስታውሳለን ። ደግሞም ዓረብ ፋቂህ ከቀለም ሰውነት ጋር ለዚሁ ታሪክ ጸሐፊነት ተለይቶ የተመደበ ሲሆን ካስታንሆዞ ግን ምድቡ ወታደር ሆኖ ይኸን የታሪክ ጽሑፍ ያዘጋጀው በወታደርነት ሥራው ላይ በመደረብ ስለሆነ በዚሁ በተ ወልን ማስታወሻ እመስግነን አሁን ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ ።

ክርስቶፎሮስ ዱጋማ ከነጦሩ ወደ ሠፈሩ ከተመለሰ በኋላ ወደ ምጥዋ ተልከው የነበሩት ፖርቱጋሎች ከባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ጋር ተመልሰው መጥተው ወደ መር ከቦቻቸው ለመጠጋትና መልእክቱን ለማድረስ የቱርክ መርከበኞች እንዳስቸገሩዋ ቸውና እዚያም ሔደው መልእክቱን ሳያደርሱ እዚህም ቀርተው ጦርነቱን ሳይካ ፈሉ በመቅረታቸው እየተጸጸቱ ለአለቃቸው ነገሩት ። የሆነ ሆኖ የነርሱና ይልቁ ንም ባሕር ነጋሹ ፴ ፈረሰኛ አምስት መቶ የእግረኛ ጦር ይዞ መምጣቱ ደስ ስለ

አለው ክርስቶፎሮስ ግራኝን እየተከታተለ ውጊያውን ለመቀጠል መወሰኑን ፤ ግራኝን ለማባረር በወሰነበት ጊዜ የቆሰሉትን ባንድ ቦታ መተውና ማስታመም ስለአስፈለገ ሁሉንም ሰብስበው ለአውራጃው ሹም ለትግሬ መኰንን እንደ አስረከባቸውና ትግሬ መኰንኑ ከነባለቤቱ በደንብ እየቀለቡ ያስታመሙዋቸውን ራሱ ግራክንዱን ቆስሎ አብሮ ታማሚ የነበረው ካስታንሆ፡ ባወሳበት ላይ «ስንት ደስታና ክበሬታ ሚስቱና እርሱ እንዳሳዩን ከዚህ ተነግሮ አያልቅም» ሲል ገልጾታል ።

ቁስለኞቹ ካገገሙ በኋላ አዲስም የባሕር ነጋሹ ጦር ከደባርዋ ስለደረሰ ክርስቶፎሮስ ሰሞኑን እንደተመኘው ግራኝን በደረሰበት እየተከታተለ ለመውጋት አሰበ ። በዚህም ጊዜ ግራኝ ከጥቂት ዓመታት በፊት በወጣትነቱ ጊዜ ያለዕረፍት ዓፄ ልብነ ድንግልን ያሳድድ የነበረውን ብድር ወጣቱ ደጋማ በርሱ ላይ ሲመልስበት ፤ ከ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ዠምሮ በተደረገው ጦርነት ሁሉ በኢትዮጵያውያኑ የጦር አለቆች በነራስ ወሰን ሰገድ በድንፋታና በማጉጠጥ ያደርገው የነበረውን የተሸናፊነት ብድር በዚህ ጊዜ ሲቀበል እናያለን ። ራስ ወሰን ሰገድ እስካሁን ድል ያደረግኸውና የዘረፍኸው ይበቃሃል ትምክህት አታብዛ ወዳገርህ ተመለስ ያለዚያ መጣሁ ብሎ በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. የጻፈለት ጊዜ «በሄድክበት ሁሉ ፈልገን አባረን እንወጋሃለን አሁን ውጊያ እየፈለግን የሚመክት ነው ያጣነው ። ወዳገራችሁ ተመለሱ ባልኸው እንስማማም አገራቱ ተጠቅልላ የኛው ናት» ብለህ ለጌታህ ንገረው ብሎ የመለሰለትን እናስታውሳለን ። ነገር ግን ጊዜ ሲያልቅ የኃይለኛም ጉልበት ያልቃል በኃይለኛም ላይ ኃይለኛ አለ ። ከወታደርም የተሻለ ወታደር ከጥይትም ከጠበንጃም እንደዚሁ የተሻለ ጠበንጃና ጥይት ስለአለ ሁልጊዜ በዓለም ላይ የተሻለው ዝቅተኛውን ሲያሸንፈው ይታያል ። የሰው ልጅ ጥረት ከሌላው ለመሻል በመታገል ላይ ነው ፤ የሰው ልጅ ሕይወት ራሱ የማያቋርጥ ትግል መሆኑ ምን ጊዜም የተረጋገጠ ነው ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ ሸሽቶ የሄደበት ሥፍራ (ዞብል ወይም እመበረት) እርሱ ካለበት ከዋጅራት (ወይም ከእንዳ መኾኒ) የአሥር ቀን መንገድ መራቱን ቀጥሎም ክረምቱ ስለተቃረበና ወደ ዞብልም የሚወስደው መንገድ ረግረግ ነውና አያስሄድም ማለትን ደጋማ ሲሰማ የማሳደዱን ጉዳይ ለጊዜው አቁሞ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር በመመካከርና በመስማማት ወኃና እህል ወደሚገኝበት ወደ እሽንጌ በተለይ ወፍላ ወደሚባለው ኮረብታ ሄደው ክረምትን በዚያ ለማሳለፍ ወሰኑ ። በዚህም ቦታ ሆኖ ስሜን ከሚገኙት ከንጉሡ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ለመገናኘትና እስካሁን የተደረገውን የጦርነት ሁኔታ ጭምር ለማስረዳት በዝርዝር ጽፎ ወደ ንጉሡ ለመላክ ደብዳቤውን አዘጋጅቶ ሲጨርስ ከዚህ በፊት ተልኮ ወደሸዋ ሄዶ መልስ ያመጣለትን ከሸዋም ከንጉሡ ጋር ሆኖ ወደዚሁ ወደ ትግሬ የመጣውን አሪያስ ዲያዝ የሚባለውን መልሶ ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ እንደላከው ጸሐፊው ያመለክታል።

## ምዕራፍ ፳፱

## የአቤቶ ሚናስ ወደ ዘቢድ ባሻ መላክ — ግራኝ አህመድ አዳዲስ የጦር መሣሪያና የቱርክ ወታደር ከዓረብ አገር እንዳስመጣ (፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ሚያዝያ - ነሐሴ)

ባለፈው በሰሀርት ጦርነት ግራኝ ቆስሎ ከሸሽ ወዲህ የሄደበት አቅጣጫ ካስታንሆዞና ጀምስ ብሩስ እንደሚሉት ወደ ዘቡል መሆኑን አንብበናል (1) ። በኢትዮጵያ አሽናፊነቱ በተረጋገጠበት ዘመን የትም ዞሮ ለመኖሪያ የመረጠው ለምለሙን ደምቢያን ሆኖ ሳለ አሁን ተዋግቶ ከቆሰለ በኋላ ወደ ደምቢያ ወደ ለምለሙ አገር በማዝገም ፈንታ ወደ በረሃማው ወደ ዘቡል (ደንከል) አገር መሸሹ ይህ ዘቡል ለቀይ ባሕር ስለሚቃረብ በአሰብ (አውሳ) ወደብ በኩል ከዘቢድ ባሻ ጋር ተላልኮ እነዚህን ሳያስበው ተዋግተው ከመቁሰል ያደረሱትን ፈረንጆች ከነርሱም ጋር የነበሩትን ኢትዮጵያውያን የሚያጠቃበት አዳዲስ የጦር መሣሪያና ወታደር ለማስመጣት እንዲመቸው ነው ። ገርርም ሉቦ በጻፈውና ለግራ ወደ ፈረንሳዊ በተረጐመው መጽሐፍ ላይ ግራኝ የሸሸበትን ሥፍራ በራሱ አጠራር "MEMBERT" ወደ መምበረት ተራራማ ሥፍራ ብሎት ይገኛል ። እንኮበር አጠገብ ያለውን የእመምሕረት ቤተ ክርስቲያን ያለበትን ወረዳ ባላገር ዛሬም እመበረት ይለዋል ። ይኸኛው ም ለዘይላ ወደብ ስለሚቀርብ በዚህም ላይ ዙሪያ ገቡ ገደላማ ስለሆነና ለመከላከል ስለሚመች ወደዚሁ መጥቶ ይሆን ? (2) ።

የሆነ ሆኖ ቀድሞ ዓፄ ልብነ ድንግልፕSያ©ጠቃበት ያመራሩ ዘዴ ጥንካሬው ድፍረቱ ተንኰሉ ቢጨማመርም ዋናው ምክንያት በመሣሪያ ልዩነት የተነሣ መሆኑን በሚያውቅበት መጠን አሁን ደግሞ ባሁኑ ጦርነት በምጥዋ በአርኪቆ ወደቦች በደባርዋ በአምባ ሠነይት እንደሚገባ እየጠበቀ ሳይከላከላቸው በቻልታ ወይም በመናቅ ያሳለፋቸው መነኩሴዎች እያለ የተሳለቀባቸው የፖርቱጋል ወታደሮች በድፍረት ፊት ለፊት ጦርነት ገጥመው ፲፭ ዓመት ሙሉ ተደፍሮ የማያውቀውን በጠበንጃ ጥይት አቁስለው ከመሸሽ ያደረሱት በመሣሪያ ልዩነት መሆኑን በደንብ እንደሚገነዘብ የታወቀ ነው ። እንደ አጋጣሚ ያች በራሱ ላይ ተነጣጥራ የተተኰሰችው ጥይት ባታቆስለው ኖሮ በፈረስ አጐዳ እንደሚደመስሳቸው ፖርቱጋሎቹ ራሳቸው አምነዋል ።

ቱርኮች ግብፅን እንደ አውሮፓ ቍጥር ፲፭፻፲፯ ዓ. ም. ከያዙ ወዲህ በግብፅ ዙሪያ ያሉትን አገሮች ሱዳንን ዓረብን በየጊዜው እያስገበሩ በየዋናው ከተማ ላይ አንዳንድ ባሻ ከራሳቸው የቱርክ ተወላጅ ወይም ከልብ የተገዛላቸውንና ያመኑትን ያገር ተወላጅ እየሾሙ ይገዛሉ ። እንደዚሁም የመንን ዘቢድን አደንን ሁሉ እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፴፰ - ፴፱ ዓ. ም. በሶሊማን ፓሻ አማካይነት ከያዙት ወዲህ በተለይ በዘቢድ የወደብ ከተማ የሚቀመጠው ባሻ ራሱ የቱርክ ተወላጅ መሆኑን

(1) Voyage de Bruce-Vol. II. የካስቴራ ትርጉም ገጽ 198 - 199
(2) Relation Historique JER. LOBO በለግራ ትርጉም ገጽ 91

ከዚህ በፊት ያነበብነው ትዝ ይለናል (1) ። በአሁኑ ሰዓት ይኸው የዘቢድ ባሻ በአ ጠገቡ ፲ሺ የቱርክ ምርጥ ወታደር እንደነበረው ካስታንሆዞ ያረጋግጣል (2) ።

ከዚሁ አያይዞ ግራኝ አህመድ ከፖርቱጋሎች ጋር ተዋግቶ ድል መሆኑን የታላቁ የቱርክ መንግሥት ተገኘ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያን በመላ ካስገበረ በኋላ አሁን በፖርቱጋሎች ወገ.ያ ተሸንፎ ይህ ታላቅ አገር ከእጁ ቢወጣ ታላቅ ጉዳት መሆኑን በማሳሰብ የጦር ወታደርና መሣሪያ እንዲልክለት ወደዚሁ ወደ ዘቢድ ባሻ በምሥጢር እንደላከበት ያመለክታል ። ይኸን መልእክት በፍጥነት ወደ ዘቢድ ፓሻ በላከ ጊዜ ለማባበያ ብዙ ገጸ በረከት ጨምሮ ነው ። ከተላከው ገጸ በረከትም ውስጥ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ግንቦት ፳፭ ቀን በተደረገው ጦርነት ተማርኮ እስካሁን ከርሱ ጋር የቆየው አቤቶ ሚናስ ይገኛል ። ስለዚህ በሰሀርት ከተዋጋበት ከመጋቢት ፳፱ ቀን ዠምሮ ይህ የጠየቀው ርዳታ ደርሶት እስከተዋጋበት እስከ መስከረም ፲ ቀን ድረስ ያለውን ብርቅ የሆነውን የአምስት ወር ጊዜ ግራኝ አህመድ በደንብ እንደ ተጠቀመበት ይታያል (3) ።

ለግራኝ አህመድ ከዘቢድ ፓሻ ዘንድ የጠበቀው ርዳታ ደርሶት ከክርስቶፎሮስ ጋር እንደገና ተዋግቶ ማሸነፉን እስክንመለከት ድረስ ስለአቤቶ ሚናስ ምርኮ ማንበብ ታሪኩን ያሙዋላዋል ። ስለዚህ መስፍን ጉዳይ እንደዚያው እንደ ግራኝ ተረታዊ አነጣሥ ወይም ቦካን ጦር አውርድ ብለው ዓፄ ልብነ ድንግል ተሳሉ እንደሚለው የመሰለ የ...ይታመንና መሠረት የሌለው አተራረክ እስከዛሬ በቆየን በብሔራዊ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል ።

በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኘው ሊታመን የማይችለው ጽሑፍ ስለአቤቶ ሚናስ እንደዚህ ይላል «ሚናስን እቴጌ እሌኒና (ሰብለ ወንጌል ማለቱ ነው) ዓፄ ገላውዴዎስ ተማክረው ወደ ፖርቱጊዝ መንግሥት የነፍጥ መያዣ አድርገው ልከውት ነበር (4) ። ስለዚህ ኑር መሐመድ የተነሣ ጊዜ ሁለተኛ ረዳት ስደዱልን ብለው ኢትዮጵያውያኑ ቢልኩ የፖርቱጊዝ መንግሥት ሚናስን በካቶሊክ ሃይማኖት አስገብቶ አስቀብቶ አንግሦ አንድ ጳጳስ ሰጥቶ ጦር ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው ። ከዚያ ሚናስ ኑር መሐመድን ድል ስላደረገ መንግሥቱን እጅ አድርጎ እንጦጦ ላይ ተቀመጠ ። ጳጳሱም ካቶሊክ ስለሆነ አንድ ዓመት ሙሉ ሲቀመጥ ከጐንደር ከትግሬ ከሸዋ ቅስናና ዲቁና ልቀበል የሚል አንድም ሰው አልመጣ አለ ። ጐጃሞች ግን እምነታቸው ቅባት ስለሆነ መጥተው ከካቶሊኩ ጳጳስ ቅስናና ዲቁና ተቀበሉ ።

በዚህ ጊዜ ከደብረ ሊባኖስ ቄስ ዓፄ ዮሐንስ ፤ ጽራግ ማሰሬ ዘመለኩት የሚባሉት መጥተው ሃይማኖትህ ምንድነው ብለው ጳጳሱን ቢጠይቁት ሃይማኖቴ አንድ

(1) Histoire de l'abissinie A.H.M. Jones-E. Monroe. ገጽ 113 - 115

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 16 ገጽ 51

(3) ጀምስ ብሩስ የወፍላውን ጦርነት እንደ አው. ቆ. ነሐሴ ፴ ቀን ያለው ትክክል አይመስልም ገጽ 199 ።

(4) አንዳንዱ ደግሞ አውረድዎ ለሚናስ ሕፃን ምድረ ርም ይላል ይኸም እውነት አይደለም ።

አካል ሁለት (የሰውነትና የመለኮት) ባሕርይ ነው ። በዚህም መለኮት የመለኮትነትን ሰውነት የሰውነትን ባሕርይ ይሠራል አላቸው ። እነርሱም "የእንጦጦ መምር አይናገር ቢናገር ባመት ያውም ሬት" ብለው አውግዘውት ሄዱ እርሱም (ጳጳሱም) ተቀሠፈ» ።

የፖርቱጊዝ መንግሥት ሚናስን ካቶሊክ አድርጎ ካቶሊካዊ ጳጳስ ጨምሮ ከወታደር ጋር ወደ ኢትዮጵያ ልኮት ከኑር መሐመድ ጋር ተዋግቶ አሸነፈ የሚለው ምንም መሠረት የሌለው የፈጠራ ወሬ ነው ። የካቶሊክ ጳጳስ የሚለው ዮሐንስ ቤርሙዴዝን እንደሆነ እርሱ እነሆ የመጣው ከጦር ርዳታው ከነክርስቶፎሮስ ዱጋማ ጋር ነው ። ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በመጣበት ሰዓት ሚናስ በግራኝ እጅ ነው ። እንድርያስ አቢዩዶን እንደሆነ አቢዩዶም በመጣበት ባፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ሚናስ በግዞት ለዘቢድ ፓሻ ተልኮ የሚቀመጠው በቀይ ባሕር ማዶ በዓረብ አገር ነው ። ሚናስ ወደፊት እንደምናነበው በግራኝ ልጅ ተለውጦ በወንድሙ በገላውዴዎስ ዘመን መጥቶ በነጋሢነት የተተካ ጊዜ ከሚሲዮኖቹ መሪ ከዚሁ ከእንድሬያ አቢዩዶና ከተከታዮቹ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ጋር ከዓፄ ገላውዴዎስ የበለጠ ጠብ አድርጓል ።

ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንዳነበብነው ግራኝ አህመድ ያፄ ልብነ ድንግልን ባለቤት ልጅ ለጋብቻ ጠይቆ እምቢ ያሉት ጊዜ በአዲስ ኃይልና ቁጣ ተነሥቶ በወጋቸው ሰዓት ኤሚር ኡመር የሚባለው የጦር አለቃው ፲፭፻፴፩ ዓ.ም. ግንቦት ፳፩ ቀን ሚናስን ማርኮ ለግራኝ ስላስረከበው እውነተኛው ታሪክ ነገሥት ስለዚሁ ጉዳይ «ንጉሡን በሠራዊቱ መማረክ በልጁ መያዝ ኀዘን ተጫነው» ያለውን አንብበናል (1) ።

ISIC

ከዚሁ እያይዞ ደንበኛው ታሪክ ነገሥት ሚናስ ተማርኮ በግራኝ እጅ ከገባ ወዲህ ስለሚናስ ሁኔታ ግራኝ አህመድ ከሚስቱና ከሹማምንቱ የተማከረ ጊዜ ከአማካሪዎቹ ውስጥ ግማሾቹ ያንተን ልጅ ያግባና ይንገሥ ለርሱም ሲል ክርስቲያኑ አማራው ሁሉ በፍቅር ይገዛልናል ሲሉ ግማሾቹ የለም በከተማ ብዙ የአማራ ነገድ ይወደዋል የርሱ መኖር አደጋ ነውና ይገደል ካሉት በኋላ ግራኝ ሚስቱን ድል ወንበራን ምን ይሻላል ብሎ ቢጠይቃት ይኸን ምንም ያልበደለንን የንጉሥ ልጅ ገድለን ፍዳ ለልጆቻችን ከምናተርፍ ልጃችንን ድረን ወገን እናድርገው ብላ የፊተኞቹን አማካሪዎች አሳብ ማጽደቋ ከርሷ ቀጥሎ ደግሞ ሸርፈዲን የሚባል አማካሪው መጥቶ ልጅህን ድረህ ሥልጣን ከሰጠኸው ሰው ሁሉ ወደርሱ ይገለበጥና መንግሥትህን ታጣለህ ከዚያ ወዲያ ባደረግኸው ተጸጽተህ ሥልጣንህን ለማግኘት ብትፈልግም አትችልም ። ስለዚህ ይልቅስ እንደገጸ በረከት አድርገህ ለዘቢድ ፓሻ ላከው ። ለጦር ርዳታ የላኩልህንና ለጠየቁህ እኒህ ፈረንጆቹ ፖርቱጋሎች ስለመጡ የቱርክ ወታደር ላክልኝ ብለህ ለምነው እነሆ ፈረንጆቹ ፖርቱጋሎች ስለመጡ የቱርክ ርዳታ ካላገኘህ ልትዋጋቸው አትችልም ብሎ እንደመከረውና ግራኝ አህመድ ከሁሉም የዚህን ሰው ምክር ተቀብሎ እስካሁን ከሁለት ዓመት በላይ ከርሱ ...

ወተእኅዞተ ወልዱ ፡

(1) ወተጻደቀ ኀዘን ለንጉሥ በተጼውዎተ ሠራዊቱ

ጋር በምርኮኛነት ያስቀመጠውን ሚናስን ለዘቢድ ፓሻ እንደላከለት በዝርዝር በግዕዝ ቋንቋ ተርኮት ይገኛል (1) ።

ነገር ግን ይኸን የመሳሰለው ሐቀኛው ታሪክ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ባለመታተሙ ሁልጊዜ አንባቢ እውነተኛውን ታሪክ ከስሕተተኛው ለመለየት ሲቸገር መኖሩ ግልጽ ስለሆነ በአሁን አጻጻፍ ሁለቱ ወገን እየተለየ በመሰፈሩ አንባቢ እንደሚጠቀምበት ተስፋ አደርጋለሁ ።

ስለዚህ ይህ ሁሉ ምክርና ውሳኔ የመጣው ግራኝ አህመድ ከፖርቱጋሎቹ ጋር ተዋግቶ ቆስሎ ከሸሸ በኋላ ስለሆነ ይልቅስ በንግሥት ሰብለ ወንጌልና በዓፄ ገላውዴዎስ ፈንታ ምንም እንኳን በገጸ በረከት መልክ ቢሆን ሚናስን የነፍጥና የመድፍ መምሪያ አድርጎ ወደ ዘቢድ ፓሻ የላከው ግራኝ አህመድ ነው ማለት ይቻላል ። የሚናስን የዘቢድን አገር ኑሮውንና በኋላ በግራኝ አህመድ ልጅ በመሐመድ ተለውጦ ከዘቢድ ወደ ኢትዮጵያ የመመለሱን ሁኔታ ወደፊት በሥፍራው ስንደርስ እስክንመለከት ድረስ ወደ ዋናው ታሪክ እንመለስ ።

በአሁን ሰዓት በግራኝ አህመድ ላይ የደረሰው የመሸነፍ ውርደት በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ዓፄ ልብነ ድንግል ከደረሰባቸው ጋር በብዙ ተመሳሳይ ነው ። ዓፄ ልብነ ድንግል ከቤተ አምሐራ ቁጥሩ የበረከተ ጦር ሠራዊት ይዘው ወደ ሽምብራ ኩሬ ሲጓዙ ግራኝ በድፍረት ቆሞ ይመከተኛል ብለው ያሰቡ አይመስልም ። ቢያስቡም [sic] ጦርነቱ እንደተዠመረ እስላሞቹ ተሸንፈው የሚሸሹ ስለመሰላቸው እስላሞቹ እንዳያመልጧችሁ ብለው ለጦር አለቆቻቸው አስጠንቅቀው እንደነበረ ፤ ለምርኮኛ መጫሪያ ገመድም ተዘጋጅቶ እንደነበረ በሥፍራው ላይ ያነበብነው ትዝ ይለናል ።

እንደዚሁም ግራኝ አህመድ በዚህ በሰሀርት ጦርነት ክርስቶፎሮስ ዳጋማ ቍጥሩ ያነሰ ጦር ይዞ ሲገጥመው በመድፈሩ መገረሙን ስለድፍረቱና ስለልጅነቱ ይቅርታ አድርጐለት ቢፈልግ ወደርሱ እንዲገባ ካልፈቀደም ወደዚህ ስሕተት ያገባችውን ሴት (ንግሥት ሰብለ ወንጌልን) ትቶ በሰላም ወዳገሩ እንዲመለስ ከጳፈለት ደብዳቤ ጋር የማትዋጉ መነኮሳት ናችሁ ብሎ የላከለትን ቆብና መቁጠሪያ ስንገነዘብ በኋላ ደግሞ በነዚሁ በናቃቸው ወታደሮች ድል ተመትቶ ራሱ ቆስሎ በቃሬዛ ላይ ሆኖ ሲሸሽ ባዔ ልብነ ድንግል የስህተት መስመር ላይ በቀጥታ መግባቱ በግ

(1) ወጸወዓ ንበይተ ሕዝቡ ወመማክርቲሁ ወይቤሎሙ ምንተ ንግበር በዝንቱ ወልደ ንጉሥ ። ወእምዝ ተሰጥዉዎ ምክረ እኩየ እንዘ ይብሉ ኢትትራኅራኅ ላዕሌሁ ወኢትምሐኮ እስከ ለሞት ወእንበለዝ ኢተአርፍ እምኔሁ ። ወበዊእ ኃበ ብእሲቱ ነገራ ዙሎ ዘይብሉ መኳንንት . . . . . ወወደየት ርኅራኄ . . . . . ወትቤሎ ኢናስሕም ላዕለ ዝንቱ ወልደ ክቡራን ነገሥት ወናሁኒ ሎቱ ከመ ይፍድየ እግዚአብሔር ለወልድነ ፍዳ ሠናየ . . . ነሀቦ ወለተነ ወንግበር ሎቱ ከብካበ . . . . . . ወተንሥአ እሐዱ ተመያኒ ወመጽአ ኃበ ግራኝ ወይቤሎ . . . . . ቦኑ ፈቀድከ ከመ ተሀብ ክብረከ ለባዕድ ወታገብእ መንግሥተከ ። እመሰ ወሀብኮ ወለተከ ይመስሎሙ ለሠራዊትከ ዘሀደገ መንግሥተከ . . . . . ለዝንቱ ወልደ ንጉሥ ፈንዎ እምሀ ለበሻ ዘቢድ ወበሎ ፈኑ ሲተ አሽከር ። አፍርንጅኒ ናሁ ወጽኡ ወኢትክል ተጻብዖቶሙ እንበለ ቱርክ ። ዛቲ ምክር አደመቶ . . . . . ታሪክ ነገሥት ፤ ገጽ 118 - 120 ።

ልጥ ይታያል ። ዳሩ ግን ዓፄ ልብነ ድንግል በግራኝ ላይ ፤ ግራኝ በክርስቶፎሮስ ላይ በመናናቅ እንደተሳሳቱ ክርስቶፎሮስ ደጋግሞ ግራኝን በመናቅ ዓፄ ገላውዴዎስ ወዳሉበት ተጉዞ ጕራውን ሳያጠብቅ ለብቻው በመግጠም ወደዚሁ ስሕተት ገብቶ ተማርኮ ከመሞት ሲደርስ እንመለከታለን ።

ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ድል በድል እያከታተለ በዋስል አድብቶ ሊያዛቸው ሲል ለጥቂት እምልጠው በጫካ ውስጥ ሆነው ግራኝ በግራ እጁ እየተማታ ሲዋጋ ዓፄ ልብነ ድንግል ዓይተውት "በሰው የተመሰለው ሰይጣን ያውና" እንዳሉት አሁን ደግሞ ከሰሀርት ጦርነት ተዋግቶ ተሸንፎ እንደሸሸ በፖርቱጋሎቻቸው ወይም በመጣሪያ ብልጫቸው አሸነፉኝ በማለት ፈንታ "ፖርቱጋሎች ሰይጣኖች እንጂ ሰዎች አይደሉም" ብሎ መናገሩን ቢርሙዴዝ ያረጋግጣል (1) ። በዚህም በወታደራዊ ተግባር ብቻ ሳይሆን ሁለቱም (ግራኝና ዓፄ ልብነ ድንግል) ሁሉን ለማድረግ የመቻልን ሥልጣን ለሰይጣን በመስጠት አንድ አንድ ጊዜ በአስተሳሰብ ሲመሳሰሉ ይታያል ።

የሆነ ሆኖ ግራኝ አህመድ ከመስፍኑ ከአቤቶ ሚናስ ጋር ለዘቢድ ፓሻ የላከውን የገንዘብ እጅ መንሻ መጠንና ዓይነት በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ የሌለውን በዮሐንስ ቢርሙዴዝ ላይ እናገኘዋለን ። እርሱም ግራኝ አህመድ ለዘቢዱ ፓሻ መቶ ሺ ወቄት ወርቅ ልኮ ከዚሁ ሃያው ሺ ወቄት ለራሱ ለዘቢዱ ፓሻ የሚሰጥ መሆኑን ከመለከተ በኋላ አገራቱን በታላቁ ጌታ (በቱርክ ሱልጣን) ስም ከያዛት በኋላ ከእጁ የወጣች እንደሆነ (ለቱርክ) እይበጅም እያለ ከማባበል ጋር ርዳታው በቶሎ እንዲደርስለት መጠየቁን ያረጋግጣል (2) ።

ስለዚህ የዘቢድ ፓሻ ከግራኝ ዘንድ የተላከውን መስፍንና ፻ሺ ለቱርክ ሱልጣን ፳ሺ ወቄት ወርቅ ለራሱ ጉቦ ከገኘ ወዲህ የግራኝ አህመድ ውድቀት በኢትዮጵያ የክርስቲያኑ መንግሥት ተመልሶ መቆም የፖርቱጋሎች አሸናፊነት የቀይ ባሕርንና በዙሪያ ያሉትን አገሮች ደህ ለሚቆጣጠረውና ለሚገዛው ለዋናው ለቱርክ መንግሥት አደጋ መሆኑን በማመዛዘን ለግራኝ አህመድ የጠየቀውን የጦር ርዳታ ላከለት ። የተላኩት የወታደሮች ቁጥር በቢርሙዴዝና በካስታንሆዞ እንደዚሁም በጆምስ ብሩስ መጽሐፍ ይለያያል ። ቢርሙዴዝ ፺፻ የቱርክ ወታደር ፳፻ ዓረብ ሲያደርጋቸው (3) ካስታንሆዞ ፱፻ ባለ ጠበንጃ የቱርክ ወታደሮች ፤ ፴ ባለ ፈረስ ወርቅ እርካብና የብረት ጫማ የተመታባቸውን ፈረሶች ተቀምጠው የሚዋጉ ፈረሰኞች ቍጥራቸው ያልተለዩ ዓረቦች ፤ አሥር የሚሆኑ መድፎች ያደርጋቸዋል (4) ። በበኩሉ ጆምስ ብሩስ የቱርኮቹን ቍጥር በማሳነስ የነፍጠኛው የቱርክ ቍጥር ፩፻ ብቻ ፈረሰኛው ተዋጊ ፪ሺ ፤ የእግረኛው ቍጥር የበረከተና ብዙ መድፍ እንደሆነ

(1) Histoire du christianisme ገጽ 124
(2) " " " 126
(3) " " " 130
(4) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 16

ያመለክታል (1) ። የሆነ ሆኖ ወታደራዊ ነክ በሆነው ጉዳይ በዚህም ላይ ጦርነቱን የተካፈለ በመሆኑ ከሁሉም የካስታንሆዞ አጻጻፍ የሚታመን ይመስላል ።

ግራኝ አህመድ ከዘቢድ ፓሻ የተላላከውና ይህን ሁሉ ርዳታ ያገኘው ከሚያዝያ ወር ዠምሮ እስከ ነሐሴ ወር ድረስ ባለው የክረምት ወራት ነው ። ይህም ወሬ በማንም ዘንድ በተለይም ሰምተው የበቃ ዝግጅት አድርገው እንዳይቋቋሙት በማለት በንግሥት ሰብለ ወንጌልና በፖርቱጋሎቹ ዘንድ እንዳይሰማ በጥንቃቄና በምሥጢር ተይዞ እንደነበረ ካስታንሆዞ በዚሁ ምዕራፍ ያረጋግጣል ። በዚህ ዓይነት በምሥጢር የመጣው መሣሪያና የቱርክ ወታደር በሚቀጥለው በወፍላ ጦርነት ተዋግቶ ያለፈ ቁጭቱን ሲወጣ ዠግናውና በክርስቲያናዊው መንግሥት ውድቀት የተናደደው ይኸንንም ለመበቀል በጋለ መንፈስ ታጥቆ የተነሣው ክርስቶፎሮስ ዳጋማ በሚያሳዝን አኳኋን ተማርኮ በሥቃይ ሲሞት ወደፊት እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፲፰

## የክርስቶፎሮስ ዳጋማ ስሜን ደርሶ መመለስ — ከእሽናፊ ጋር የመደረብ ግዴታ

በግራኝ አህመድ ኃይልና ተቆጣጣሪነት ምክንያት የክርስቶፎሮስ ዳጋማ ጦር ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ሆኖ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ተገናኝተው ኃይላቸውን የበለጠ ለማጠንከር አልቻሉም ። በአሁኑ ጊዜ ግራኝ አህመድ ዞብል ሆኖ ሳያስበው እመቁሰል ያደረሰው የፖርቱጋሎቹን ጦርነት በደንብ ለመበቀል የሚያስችለውን የጦር ወታደርና መሣሪያ በጥንቃቄና በምሥጢር በሚሰበስብበት ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌልና እነ ክርስቶፎሮስ ዳጋማ በሰሀርት ድልን ከአገኙ ወዲህ እሽንኄ መጥተው በወፍላ ተቀምጠዋል ።

በበኩላቸው ወጣቱ ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡበት ዓመት በ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. በታኅሣሥ በትግሬ ከነገራድ ኡስማንና ከከሐዲው ከድልበ ኢየሱስ ጋር ፤ በስሜን ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ከነወዚር ሙጃሂድ ጋር ከተዋጉ ወዲህ ከስሜን ወደ ሸዋ በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ተዛውረው ከግራኝ አህመድ ልጅ ከናስር አድ ዲን ጋር በደዋሮና በይፋት መዋጋታቸውንና ከሸዋ ደግሞ ወደ ስሜን እንደገና ከማርቆስ (አርያስ ዲያዝ) ጋር መመለሳቸውን አንብበናል ። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ይኸውም ማለት በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. መጨረሻና በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መዠመሪያ ወራት ላይ ከሸዋ ወደ ስሜን ተዛውረው ባሉበት ሰዓት ግራኝ አህመድ ገላውዴዎስና ፖርቱጋሎቹ ምንም እንኳን እንዳይገናኙ ቢጥር ወደ ዞብል ቆስሎ በሸሸበት የአምስት ወር ጊዜ ውስጥ ሁለቱን ለመገናኘት የከለከላቸው እንቅፋት አይታይም ። ምናልባት ከግራኝ ቁጥ

(1) Bruce.......Vol. 2 ገጽ 199 ።

(2) Histoire de l'abissinie-Jones et Monroe 115-116. Historia geral de Ethiopia-a-115-116 Historia geral de Ethiopia -a-lta B. TELLEZ XIII 165 Editora 1936.

ጥርና ንጉሡ ካሉበት ርቀት በቀር ከሚያዝያ እስከ መስከረም ያለው ጊዜ የክረምት ወራት በመሆኑ ጅምላውን ጦር ከጓዝ ጋር የተከዜ ወንዝ አላሻግር ብሎ ይሆናል ።

ቢሆንም እኚህ ወጣት ንጉሥ ከመጡት ፖርቱጋሎች ጋር ሳይገናኙ ብቻቸውን ቍጥሩ ያነሰ ጦር ይዘው ሲመቻቸው እየተዋጉ ሳይመቻቸው እየሸሹ ከትግሬ ወደ ስሜን ከስሜን ወደ ሸዋ ከሸዋ ወደ ስሜን እየተዘዋወሩ ሲያሸንፉም ሲሸነፉም ባያሸንፉም ቅሉ በዚያን ጊዜ ጉዞ በግራኝና በሹማምንቱ ጥብቅ ቍጥጥር ውስጥ እያለፉ የግራኝን ጦር ባንዳንድ ቦታ ማስቸገራቸውና የደኅንነትና የትንሣኤ ቀን ለጠማው ክርስቲያናዊ ሕዝብ የድል ጮራ ለማሳየት መቻላቸው ያነሰውን የርሳቸውን ጦር የበረከተው የግራኝ ጦር ለመደምሰስ አለመቻሉ አስገራሚ ነው ።

ቢሆንም ይኽን ሁሉ ሲችሉ እርሳቸው ሄደው ወይም እናታቸውንና ፖርቱጋሎቹን ወደ እሉበት አስመጥተው ለመገናኘት ሳይችሉ እንዲያውም የግራኝ ጦር አጥቂነት ስለተሰማቸው በአሁኑ ሰዓት ከዚያው ከትንሹ ጦራቸው ጋር ከስሜን ወደ ጋፋት ተዛውረው የግራኝ ጦር ሊደርስ በማይችልበት ተራራማ ሥፍራ ተቀምጠዋል (1) ። ይሁን እንጂ የመገናኘቱ ጉዳይ ቢያዳግትም በማርቆስ አማካይነት መላላካቸውና የመልእክት ግንኙነታቸውን እንዳላቋረጡ ይታወቃል ። ወጣቱ ንጉሥ ሲመች አደጋ እየጣሉ ሳይመች ደግሞ ወደ ተራራማ ሥፍራ እየሸሹ ራሳቸውን በሚጠብቁበት ፣ ግራኝ አህመድ ዞ[illegible]ሮኖ ጦር በሚሰበስብበት ጊዜ በበኩሉ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ሥራ እንዳልፈታ በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ ይነበባል ። በዚሁ መጽሐፍ እንድ ይሁዳዊ (2) ካንድ ቀጥ ካለ የተራራ አገር (3) ወደ አሸንጌ መጥቶ ንጉሡ (ዓፄ ገላውዴዎስ) ሊተላለፉ የሚችሉበትን ተራራ እስላሞች ስለያዙት እኔ እየመራሁ ልውሰድህና ተራራውን ከእስላሞች አስለቅቅ ብሎ እንደመከረው በዚህ ምክንያት ክርስቶፎሮስ ለሕዝቡም ለግራኝም የጦር ሠራዊት አገሩን ለቀው የሸሹ ወይም የሄዱ እንዳይመስላቸው ብዙውን ሠራዊት እዚሁ አሸንጌ ላይ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ትቶ እርሱ ፩፻ የሚሆኑ የተመረጡ የፖርቱጋል ወታደሮች ይዞ በምሥጢርና በግሥጋሤ ወደ ስሜን ተራራ መዝመቱን ያረጋግጣል(4)።

ከዚሁ አያይዞ ክርስቶፎሮስና ጦሩ ስሜን የእስላሞቹ ጦር በሠፈረበት በኩል በመሪያቸው አማካይነት ደርሰው ወታደሮቹ ከእስላሞቹ ወታደሮች ጋር ገጥመው ሲዋጉ ራሱ ክርስቶፎሮስ ከእስላሞቹ መሪ ከሲዲ መሐመድ ጋር አንድ ላንድ በፈረስ ላይ ሆነው ሲደባደቡ ክርስቶፎሮስ ሲዲ መሐመድን በሰይፍ በትር መትቶ እንደ ጣለው እርሱም ሲወድቅ እስላሞቹ ግማሾቹ እየተዋጉ ሲሞቱ የቀሩት እንደሸሹ በዚያም ብዙ የሐብትና የፈረስ ምርኮ እንደተገኘ ከዚህ ድል በኋላ ይኽንኑ የተያዘ

(1) Histoire du christ-de la croze ገጽ 198

(2) ፈላሻ ማለት ነው ፤

(3) ስሜን ማለቱ ነው ፤

(4) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕ. 17

ውን ተራራማ አገር በፈቃዱ ክርስቲያን ለሆነው ለይሁዲው አስረክቦ የተራራውን ነፃ መሆን ላቄ ገላውዴዎስ በመልእክት እንዲነግር አዞ እርሱ ወደ አሸንጌ ወደ ወገኖቹ ተመልሶ መቀላቀሉን ይገልጽና ለግራኝ ከዓረብ አገር የጦር መሣሪያውና ወታደሩ ለርዳታ የደረሰለት ቀንና ክርስቶፎሮስ ከስሜን ተመልሶ አሸንጌ የደረሰበት ሌሊት አንድ መሆኑን ካስታንሆዞ በመጽሐፉ ያመለክታል (1)። እዚህ ላይ ሲዲ መሐመድን የተዋጋና የገደለ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ሲሆን ያቄ ገላውዴዎስን ዜና መዋዕል ያዘጋጀው ጸሐፊ የሲዲ መሐመድን ገዳይ ዓፄ ገላውዴዎስን አድርጎቸዋል (2)። ምናልባት ዜና መዋዕል ጸሐፊው ሲዲ (ሰይድ ወይም ሰዓድ) መሐመድን የገደለው ክርስቶፎሮስ ሆኖ ሳለ ግድያውን ለንጉሡ የሰጠበት ምክንያት በርሳቸው ዘመን በየትም ክፍል ማናቸውም ሹም ቢገድል በርሳቸው ስም አድርጐት ይሆናል። ይኸም በኢትዮጵያ የአጻጻፍ ታሪክ ውስጥ የተለመደ ነው።

እንግዲህ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ስሜን ሄዶ የተዋጋበትና ቱርኮቹ ለግራኝ ርዳታ የደረሱበት ወሩ ነሐሴ ዓመቱ ያው ፲፭፻፴፬ ዓ.ም. ሲሆን የተዋጉበት ደግሞ በመስከረም ወር (፲፭፻፴፭ ዓ. ም.) መሆኑን እነሆ በሚቀጥለው እንመለከታለን።

እንደተለመደ በዚህ በስሜኑ ዘመቻ ቤርሙዴዝ ከካስታንሆዞ የተለየ አተራረክ ሲያቀርብ እንደዚህ ይላል «ክርስቶፎሮስ ፖርቱጋሎችና ትንሽ መንገድ የሚመሩትን ያገሩን ሰ[illegible]ይዞ ሄዶ ከሹሙ ጋር ተዋግቶ ፳ ሰው ገድሎ ፴ ፈረሶች እንደ ማረከ የቀሩት ሸሹ። በዚያን ጊዜ የተራራውን መንገድ የሚያውቁት አይሁዶች እየተከታተሉ የሸሹትን ከነሹማቸው ገደሉዋቸው»። ከዚህ በማያያዝ (ፈላሾቹ) የተማረከውን ብዙ ዕቃና ሴት ይዘው የሹሙን (3) ጭንቅላት ቆርጠው ወደ ክርስቶፎሮስ መጥተው እንዳስረከቡት፣ ከተማረኩት ሴቶች መካከል በጣም ቆንጆ የሆነችው የሹሙ (ሲዲ መሐመድ) ሚስት ስለነበረች ክርስቶፎሮስ ለራሱ ስለወሰዳትና ሹማምንቱ ዓይናቸውን ጥለውባት ስለነበረ ከነርሱ ጋር በቅናት ተጣልቶ እንደነበረ ያመለክታል (4)።

በዚህ ዓይነት በአይፈርስ በባሌ ጦርነት የነአዝማች አዳሉ ባለቤቶች ያሸናፊ ሚስት ይሆኑ እንደነበረ፣ የተሸናፊ ጭንቅላትም እየተቆረጠ ለአሸናፊው ለግራኝ ይቀርብ የነበረው አሁን ደግሞ ነገሩ ተዘዋውሮ የእስላሞቹ ሹማምንት ሚስትና ጭንቅላታቸውን ለአሁኑ አሸናፊዎች መገበር ጀምረዋል ማለት ነው። የመካከለኛው ዘመንና እስከ ቅርብ ጊዜ ያለው የዓለም ጦርነት ሁኔታ ይኸን በመሳሰለው ድርጊት መፈጸሙ የታወቀ ነው።

(1) የፖርቱጋሎች ዝማንነት ምዕ. 17 ገጽ 47

(2) ወገብረ ፀብአ ምስለ ኃያላኒሁ ለኢማም አህመድ ወሞያሙ ወቀተሎ ለሰዒድ መሐመድ ሊቀ ሠራዊተ ፀብእ.....ዛቲ ይእቲ ቀዳማዊት መዊዕ ዘኮነት በእዴሁ ለግር ገላውዴዎስ። የገላው. ዜና መዋዕል ገጽ 21

(3) ሲዲ (ሰዓድ) መሐመድ መሆኑ ነው፣

(4) Histoire du christianisme ........ ገጽ 129

ዜና መዋዕሉን የጻፈው የሲዲ መሐመድን ገዳይነት ለጌታው ለዓፄ ገላውዴ ዎስ እንደሰጠ ቢርሙዴዝ ደግሞ በዚህ አጻጻፉ ገዳዮቹን ያገር ተወላጆቹ (ፈላ ሾች ?) አድርጓቸዋል ። መቼም በጦርነቱ ላይ ሦስቱም ጸሐፊዎች የሉም ። ምናል ባት የእስላሞቹ ሹም ሲዲ መሐመድ ከክርስቶፎሮስ ጋር በፈረስ አንድ ላንድ ተደባድቦ ተመትቶ በወደቀ ጊዜ ከወደቀበት ተነሥቶ ከነጭፍራው ከሸሸ በኋላ ያገሩ ተወላጆች ፈላሾቹ ዱካውን ተከታትለው እርሱንና ወገኖቹን ገድለው ሀብቱ ንና ሴቶቹን ማርከው የሲዲን ጭንቅላት ቆርጠው ይዘው ለክርስቶፎሮስ አቅርበው እስደስተውት የሹመንም ሚስት ለራሱ ዕቁባት አድርጓት ይሆናል ። በዚሁም በፈላሾቹ መሪ ተደስቶ የተያዘውን አገር ለርሱ ሰጥቶ ዓፄ ገላውዴዎስ ያሉበት ቦታ ጋፋት ሩቅ ከመሆኑ የተነሣ ለመገናኘት ሳይችል ቀርቶ የድሉ የምሥራች እንዲደር ሳቸው አድርጎ እርሱ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ወዳሉበት ወደ ወፍላ (አሸንጌ) ተመ ልሷል ማለት ነው ።

ይህ ያሁኑ የ፲፰፻፸፱ - ፹፩ ዓ.ም. የጦርነቱ ሁኔታ ከ፲፱፻፳፯-፳፰ ዓ.ም. ከኢ ጣልያ ጦር ከተደረገው ጦርነት ጋር በጣም ተመሳሳይነት እንዳለው ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ኢጣልያ ኢትዮጵያን በመላ ለመውረር ዓድዋ ላይ በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ሞክሮ በዓፄ ምኒልክ ጦር ሠራዊት ተሸንፎ ከመረብ ወዲያ ባለው አገር ከቆመ ወዲህ በአርባ አራት ዓመታት ውስጥ ከፍ ያለ የጦር ድርጅት ካደረገ በኋላ ያለፈውን የመሸነፍ ዕፍረት ለመመለስ እ[illegible]ንገዱንም ለአገሩ ለኢጣልያ ሰፊ የቅኝ ግዛት ለመስጠት ሙሶሊኒ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ኢትዮጵያን በሌላት የጦር መሣሪያ እንደዚሁም በቦምብና በጋዝ ጭስ አሸንፎ ይዞ ፭ ዓመታት (፲፱፻፳፰ - ፲፱፻፴፫ ዓ. ም.) መግዛቱን የማያውቅ የለም ።

በ፲፱፻፴፫ - ፴፬ ዓ.ም. ላይ የእንግሊዝና የባለ ቃል ኪዳኖቹ ጦር ከኢትዮጵያ የአርበኛና የስደተኛ ወታደር ጋር በመተባበር በበርበራና በከሰላ በከረን በኬንያና በጅቡቲ የኢጣልያን ጦር እያጣደፈ እየወጋ ባሸነፈው ጊዜ የዚህም ወሬ በጐንደር በጅማ በሐረር በአስመራ በደሴ በአዲስ አበባ ሲሰማ ያገራቸው ውድቀት ለአጸጸታ ቸው ክፍሎች ወሬው ደስታ ሲሰጥ ጣሊያንን ከልቡ ያገለግል በነበረው ወገን ኀዘ ንን ፣ ሽብርን ሲፈጥር ተመልክተናል ። በ፭ቱ ዓመት የአገዛዝ ጊዜ ውስጥ በወገኑ ላይ በሠራው ወንጀል የፈራው በየቤቱ ሆኖ ወደፊት በሚደርስበት የሚያደርገው ጠፍቶት ሲጨነቅ የቀረው አገሩን ያገለገለው ወይም ለኢጣልያ ባንዳ ሆኖ መካከለ ኛና መጠነኛ አገልግሎት የሰጠው የኢጣሊያኖችን ባለሥልጣን እየከዳ ወደ አርበ ኞቹና ወደ ስደተኞቹ ዘንድ እየሄደ በመደባለቅ ስንቅ በመስጠት መንገድ በመም ራት አገልግሎቱን አትርፏል ። አንዱ ባንዳ እየተባለ ኢጣሊያኖችን ሲያገለግል ወንድሙ አርበኛ ሆኖ ስላገሩ በዱር በጫካ እየተዋጋ ያገለገለውን የማያውቅ የለም ። በአሁኑ በግራኝ የወረራ ዘመን ከአገዛዙ ጽናትና ከጊዜው ርዝመት የተነሣ አብዛኛው ሹማምንት በግድም በውድም የግራኝና የሹማምንቱ አገልጋይ ሲሆን በፊት ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር አሁንም በወጣቱ ንጉሥ በገላውዴዎስ ዙሪያ ያለው የተከላካይ ቁጥር በጣም ያነሰ ነው ። ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ፖርቱጋሎቹን

ምጥዋ በደስታ ተቀብሎ በደባርዋ አስተናግዶ ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ከደብረ ዳሞ እየመራ አምጥቶ ከፖርቱጋሎቹ ጋር በማገናኘት አገሩንና ወገኑን ሲያገለግል የርሱ የቅርብ ዘመዱ ካስታንሆዞና ቤርሙዴዝ መጠሪያ ስሙን ሳይጠቅሱ ትግሬ መኰንኑ ወይም ግራኝን ያገለግል የነበረው ከሐዲው ወደኛ መጥቶ የግራኝን በሰሀርት ጦርነት የአቆሳሰሉን ወሬ ነገረን ያሉት ከፖርቱጋሎቹ መምጣት በፊት ዋና የግራኝ አገልጋይ ነበር ማለት ነው ። በሡራዬ ሽማምንት በተስፋ ልዑልና በቴዎድሮስ መካከል የነበረውንም ልዩነት ባለፈው የተመለከትነው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ። በሸዋ የነአዝማች ሐይቢ የነአናንያ ክዳት በኢጣልያ የወረራ ዘመን ከነበሩት ከዳተኞች ጋር ተመሳሳይ ነው ።

ግራኝ አህመድና ጦሩ ወገራንና ስሜንን በአስገበረበት ጊዜ እንኳውል እነ አዝማች ዮሐንስ እየተዋጉ በሞቱበት ዓመት (፲፭፻፳፯ ዓ. ም.) የስሜን ፈላሾች በእሸናፊው በግራኝ ፊት ቀርበው በኛና በባሕር አምባ ሰዎች (ክርስቲያኖች) መካከል ከአርባ ዓመት ዠምሮ የቆየ ጠላትነት ስላለ እነርሱን እኛ ደስ በሚያሰኝህ ዓይነት እንዋጋልሃለን አንተ ዝም ብለህ ተቀመጥ ያሉትን በምዕራፍ ፺፫ አንብበናል ።

አሁን ደግሞ ዘመኑም ሁኔታውም ተለዋውጦ አዳዲስ መሣሪያ ይዘው የመጡት ፖርቱጋሎች ምጥዋ በመርከብ ገብተው የግራኝን ባሕር ነጋሽ የኑርን ጭንቅላቱን ቆርጠው ለንግሥት ሰብለ ወንጌል መላካቸው ፤ በአምባ ሠነይት የግራኝን ጦር ማጥፋታቸው በሰሀርት ራሱ ግራኝ ተዋግቶ ቆስሎ መሸሹ ሲሰማ የስሜኑ የፈላሻ ምቹ መሪ ወደ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ዘንድ መጥቶ ስሜን ድረስ እየመራ ወስዶ በሲዲ መሐመድ ከሚመሩት እስላሞች ጋር ማዋጋቱ እራሱም እየተዋጋ የሸሹትን ገድሎ ሴቶቻቸውን ማርኮ ላሸናፊው ለደጋማ ማቅረቡ በዚህም ሥራው ለጊዜው በርሱ መሪነት የተያዘውን አገር መሾሙ ከዚሁ እላይ ካወሳነው ምክንያት ጋር የተያያዘ ነው ። የዚህ ሁኔታ በበለጠ ከግራኝ ሞት በኋላ በሰፊው ሲታይ ወደፊት እናነባለን።

ምዕራፍ ፻፷፩

በወፍላ (ኰረም) የግራኝ አህመድና የፖርቱጋሎቹ መዋጋትና የፖርቱጋሎቹ መሸነፍ — የክርስቶፎሮስ ደጋማ ከፉኛ መቁሰል (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም ፫ ቀን)

ግራኝ አህመድ ከሰሀርት ጦርነት ላይ ቆስሎ ወደ ዞብል ከሸሸ ወዲህ ድምጡን አጥፍቶ ውስጥ ውስጡን የተላላከበት የጦር ርዳታ ከዘቢድ ከደረሰለት በኋላ እነዚህንና በተረፈ አጠገቡ ያለውን ከየአውራጃው የሰበሰበውን ጦር ይዞ ወደ ወፍላ (እሸንጌ) አመራ ። በዚያም ንግሥት ሰብለ ወንጌልና በግሥጋሤ ከስሜን የተመለሰው ክርስቶፎሮስ ደጋማ ከነወታደሩ ይገኛሉ ። መቼም የኛዎቹም ባይጽፉት የፖርቱጋሎቹም ጸሐፊዎች ችላ ቢሉት ነው እንጂ በዚህ ሰዓት በንግሥቲቱ ዙሪያ ተሰብስበው ከፖርቱጋሎቹ ጋር በማበር የግራኝን ጦር ለመውጋት ብዙ የክርስቲያን ሹማምንት እንደሚኖሩ ጥርጥር የለውም ።

የግራኝ ጦር ከዞብል ተጉዞ አሸንጌ ደርሶ በወፍላ ጉብታ ሥር ለጦርነት መሰለ ፉን ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ፖርቱጋሎቹ ካሉበት ቦታ ሆነው ቁልቁል ተመልክ ተው እነርሱም በበኩላቸው ለጦርነት ይዘጋጁ ዠመር ። ይህ ወፍላ የሚገኘው በካ ርታው ላይ እንደሚታየው ከአሸንጌ ሐይቅ ምዕራብ ሆኖ በዛሬው የአገዛዝ ድል ድል በወሎ ጠቅላይ ግዛት በሰቆጣ የአውራጃ ግዛት በመሐል ወፍላ ወረዳ ግዛት ውስጥ ነው ። ከተማውም ኮረም ነው ።

ስለዚህ ጦርነት ታሪከ ነገሥቱ ግራኝ በዞብል ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከፈረን ጆቹ ጋር በወፍላ ከርመው በነገሡ በ፪ ዓመት በመስከረም ፫ ቀን ተዋግተው ግብ ጣኑ "ክርስቶፎርስ" መሞቱን ካወሳ በኋላ ስለ አሟሟቱ በሌላ ሥፍራ የሚለ ውን ወደፊት እናነባለን (1) ። ግብጣን የሚለው ካፒቴን ለማለት መሆኑን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

በነገሡ በ፪ ዓመት የሚለው ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡ በ፪ ዓመት ማለቱ ነው ። ነገር ግን ዓፄ ገላውዴዎስ አባታቸው በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. መስከረም ፭ ቀን ሞተው እርሳቸው በዚያው ዓመት ስለነገሡ ያሁኑ ጦርነት የተደረገው በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም ፫ ቀን ስለሆነ ምንም እንኳን ዓመቱ ሲቆጠር ከሁለት ዓመት ባይበልጥ "በነገሡ በ፫ኛው ዓመት" ብሎ ማንበብ የተሻለ ነው ።

ይህ አሁን የምናነበው ጦርነት የተደረገበትን ቀን ካስታንሆዞ እንደ አው. ቁጥር ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. ያደረገው ሆኖ ጀምስ ብሩስ ነሐሴ ፴ ያለውን መሴ ኢኖ ሊትማን በኢትዮጵያ አቈጣጠር መስከረም ፪ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. የቅ ዱስ ዮሐንስ ምትረተ ርእሱ በዋለበት ላይ አድርገውታል (2) ። ይኸም ትክክለኛ አስተሳሰብ ስለሆነ ከታሪከ ነገሥቱ ጋር ተቃርቧል ።

የሆነ ሆኖ አሁን የጦርነቱን ሁኔታ እንመልከት ።

የወታደርና መድፍ ክርስ መቼም ለግራኝ አህመድ በስውር አዲስ የመጣለትን ቶፎሮስ ዶጋማ የተረዳው ጦርነቱ ሲዠመር ብቻ መሆኑን የካስታንሆዞ መጽሐፍ ያስረዳል ። የዚህም ምክንያት ግራኝ አህመድ ከዞብል በበረሃው በደንከል በኩል አድርጎ ወደ ዘቢድ ፓሻ ተላልኮ ጦር ያስመጠው በምሥጢር መሆኑ ባለፈው ተመ ልክቷል ። የፖርቱጋልና የክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ሰውም በዚህ በበረሃና በማያው ቀው በደንከል በኩል አልፎ ነገሩን በስለላ ሊደርስበት አይችልም ። የደንከል ሕዝብም እንኳን ሃይማኖት ተጨምሮ እንደዚሁም ቢሆን ባሁኑ ጊዜ ገዥነቱ ከ፲፭ ዓመት ዠምሮ ለጸናው ለግራኝ ታማኝና ታዛዥ መሆን አለበት ።

ስለዚህ በሁለቱ ጠበኞች መካከል ያለው የአሁኑ የጦር አሰላለፍ በመሣሪያም በወታደርም ብዛት በጣም የተለያየ ነው ። መቼም ቱርኮቹና ፖርቱጋሎቹ በዠግን ነት በጦር አመራር ዘዴ በመሣሪያ ጥራት ምንም ያህል አይተናነሱም ። ዳሩ ግን

(1) ግራኝኒ ክረመ በዞብል ወከረመት ንግሥት ሰብለ ወንጌል በአፍላ ምስለ አፍርንጅ ። ወበ፪ ዓመት እምዘ ነግሠ (ገላውዴዎስ በነገሠ በ፪ ዓመት) ገብሩ ፀብአ አመ፫ቱ ለመስከረም ወሞተ ግብጣን በወርጋ ጥቅምት ፤ ታሪከ ነገሥት ባሴት ያሳተ. ገጽ 333 ፤

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕ. 18 ገጽ 56. 95 - 96

ቀድሞ ከግራኝ ጋር በነበሩት ቱርኮችና ዓረቦች ላይ ዘጠኝ መቶ ወይም ከዚህ ያነሱ ደንበኛ ትጥቅ ያላቸው ቱርኮች በአዲስ ጉልበት ሲጨመሩ በዓረቦቹም ላይ ዓረቦች ሲታከሉ በወዲህ በኩል የመጡትን አራት መቶ ፖርቱጋሎች ግን ያለፉት የእምባ ሠነይትና የሰሀርት የስሜን ጦርነቶች ቍጥራቸውን ሞትም ቁስለትም እንዳመነመነው ተመልክተናል ። ከነዚሁ ደግሞ ክርስቶፎሮስ ፩፻ የሚሆኑትን ፖርቱጊዞች ይዞ በፈላሻው መሪነት ስሜን የሲዲ መሐመድን ጦር ወግቶ መሪውን ገድሎ የተራራውን መንገድ ለንጉሡ ለማስለቀቅ ሄዶ በድካም መመለሱን ተመልክተናል ። ሄዶ የመጣበትም የስሜን አገር ተራራማ ከመሆኑ የተነሣ የግሥጋሤው ጉዞ በከብትና በእግር ስለሆነ ጦርነቱም የተዠመረው ተመልሶ በገባ በማግሥቱ በመሆኑ ከጭፍሮቹ ጋር ጣመኑ እንኳን ሳይረግፍ ከአድካሚ ጉዞ ወደ ኃይለኛ ጦርነት ተጋብተዋል ማለት ነው ።

ይሁን እንጂ የልቡ ዠግንነት የሃይማኖቱ ጽናት የወገኑ ፍቅር የኃላፊነት ተግባሩ ወጣትነቱን ስለአጸናው ክርስቶፎሮስ ደጋማ በዚህ ቀን የተዠመረውን ይኸን ኃይለኛና ከባድ ጦርነት በሙሉ ፈቃድና በግዴታ ጭምር ተቀብሎ መርቷል ማለት ነው ።

እንደ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ አጻጻፍ የግራኝ ጦር ክርስቲያኖቹ ወደ አሉበት ተግመታየት የዠመረው ገና ክርስቶፎሮስ ደጋማ ከስሜን ሳይመለስ ነው ። የግራኝ ጦር እንደታየ በአስተኛይ ድረስ የሚል ለክርስቶፎሮስ ደጋማ መልእክት ልከው በሠፈር ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር ቀርተው የነበሩት ሹማምንት ለውጊያ መዘጋጀታቸውን ወዲያው ክርስቶፎሮስ ደጋማ የጦርነቱ ዋዜማ ዕለት ደርሶ የጦር ምክር ማድረጋቸውን (1) ፤ ከዚሁ አያይዞ በምክሩ ላይ የጦር ሹማምንቱ ባንድ ቃል የግራኝ ጦርና የኛ ጦር በብዛት ስለሚለያይ ቱርኮችም በሌሊት ከሠፈራቸው ወጥተው መዋጋት ስለማይችሉ በሁለት ወገን በሌሊት አደጋ ጥለን እንውጋቸው ብለው ቢያማክሩት እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን በዚህ ቀን ለሽሽትና ለውርደት ስለፈረደባቸው በቀን እንጂ አዘንግቼ በሌሊት አልዋጋም ብሎ ክርስቶፎሮስ መልስ ስለሰጠ ሁሉም የመሪውን ትእዛዝ ያለልቡ ተቀብሎ ለውጊያው ተዘጋጅቶ ከተራራው መውረድ ሲዠምር ፍጻሜው እንዳላማረ ሁሉ ከመዠመሪያውም ላይ ከኛ አንድ ፈረስ የኛዎቹ ሲይዙት ሲከተሉት አምልጦ ወደ ጠላት ሠፈር ገባ ከማለት ጋር ይኸው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ የክርስቶፎሮስን የእምቢታ ውሳኔና አመራር ከመንቀፍ ጋር ይጽፋል ።

ሚጉኤል ደ. ካስታንሆዞ በበኩሉ የግራኝ አህመድ ጦር ከሠፈሩ አጠገብ መጥቶ በብዛት ሲታይ ይልቁንም ጦርነቱ ከተዠመረ በኋላ ከመድፉና ከጠበንጃው ተኵሶ ብዛት የተነሣ ለግራኝ አህመድ አዲስ ጦርና መሣሪያ እንደደረሰው ክርስቶፎሮስ ስለተረዳ ከመዠመሪያው ላይ ከሜዳ ወጥቶ በመግጠም ፈንታ አሉበት አጥር ውስጥ እንዳሉ (2) መከላከልን እንደመረጠ ፤ ነገር ግን ከውጭ የሚተኰሰው

(1) Histoire du christ ገጽ 130 - 132 Historia geral...B. TELLES ምዕ.
(2) የደንጊያ ካብ ወይም የአፈር ድድቅ ይመስላል ፤

የጠበንጃና የመድፍ ጥይት በብዛት እየመታ ስለጐዳቸው አጥሩም ምንም ያህል ስለአልጠቀመ እስላሞቹም እያደር እየተጠጉ ማጥቃት ስለጀመሩ የበታቹ ሹማም ንት ጭፍሮቻቸውን ይዘው እየወጡ እንዲዋጉ ትእዛዝ ሰጥቶ እርሱ ራሱም ሃምሳ የሚሆኑ ወታደሮች አስከትሎ ወጥቶ በማንባሩ የሚገኙትን ፩፻ የሚሆኑትን ቱር ኮች ወግቶ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ ማድረጉን ይገልጻል (1) ።

ይሁን እንጂ ተዋግቶና ብዙ ጉዳት አድርጎ ሲመለስ አራቱን ጭፍሮቹን ገድ ለው ብዙዎቹን እንደ አቆሰሉበት እርሱም ራሱ በጠበንጃ ጥይት አንዱን እግሩን እንደ ቆሰለ ። ባንደኛው ወገንም እንደዚሁ ቱርኮቹ በጣም አስጨንቀው በሚዋጉ በት ጊዜ ማንኤል ዳ ኩንሃን በርትቶ በመዋጋት ወደኋላ እንደ መለሳቸው እርሱም እንደዚሁ ሲመለስ የርሱን ፮ ሰዎች ገድለው ብዙዎቹን እንደ አቆሰሉበት ካስታን ሆዞ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ይገልጻል ።

ጸሐፊው ካስታንሆዞ "በዚህ ጦርነት ክርስቶፎሮስ ምንም ቢቆስል ወዲያና ወዲህ እያለ እየተዘዋወረ በማደፋፈር በእልቅናው የሠራውን ተግባር የምገልጥ በት ቃል አላገኘም" ሲል አድንቆታል ። ንግሥት ሰብለ ወንጌልም በቤታቸው ሆነው የሚደረገውን ጦርነት በማየት በትልቅ ኀዘን እያለቀሱ ቤታቸው በቁስለ ኞች መልቶ እርሳቸውና ደንገጡሮቹ ቁስላቸውን ያሥሩላቸው እንደነበረና በዚህ ቀን ንግሥቲቱ ጠቃሚ ሥራ መሥራታቸውን ከውጭ የሚተኮሰው ጥይት አንዳ ንድ ጊዜ ካሉበት ቤት እየደረሰ ሁለቱን ደንገጡሮች እንዳቆሰላቸው ያረጋግጣል ።

አሁንም የቱርኮቹ አጥቂነት እየጠነከረ መሄዱን ክርስቶፎሮስ ሲመለከት ፍራንሲስኮ ዲ አብሬውን ከሰዎቹ ጋር ወጥቶ እንዲዋጋ ላከው ሲመለስም ቱርኮቹ ጉዳት እንዳያደርጉበት ሲል ወንድሙን ኤኖፍሬ ዲ አብሬውን ከርሱ በኋላ አስከ ትሎ ልኮት ሁለቱም ወጥተው ሲዋጉ በጥይት ተመትቶ የመዠመሪያው ሲወድቅ ሁለተኛው ወንድሜን እነሣለሁ ብሎ ወደዚያ ሲያመራ እርሱም ተመታና ሁለ ቱም ሞቱ ።

በእንደዚህ ዓይነት ውጊያው እስከ ቀትር ድረስ ከቀጠለ በኋላ ተዋጊው ሁሉ (የፖርቱጋል ንጉሥ) ሰንደቅ ዓላማ ወደ አለበት እንዲሰበሰቡ አድርጎ አሁንም እን ደገና ኤማኑኤል ዳ ኩንሃን ወደፊት አልፎ የግራኝን ጭፍሮች እንዲገጥም ደጋማ ስለአዘዘው እየፎከረ ሄዶ በመዋጋት ወደኋላ መለሳቸው ። ሌሎቹም ፖርቱጋሎች እንደዚሁ በፉከራ እየወጡ ሲዋጉዋቸውና አጥቅተው ሲመለሱ የግራኝ ጭፍሮችና ቱርኮች በብዛት እንደገና እየደጋገሙ ከመልስ ላይ ብዙ ሰው ፈጁባቸው ። በዚሁ ጊዜ ራሱ ክርስቶፎሮስ ገና አስቀድሞ እርሱን ስታዩ በሮምታ ተኩሱበት የሚል የግራኝ ትእዛዝ ስለነበረ ተኩሰው እንደገና ቀኝ ክንዱን በጥይት ክፉኛ ቆሰለ ። በዚ ያን ጊዜ ዳ ኩንሃን እየፎከረ በግራኝ ጭፍሮች ላይ ገብቶ ቁስለኛውን አለቃውን ክርስቶፎሮስን ይዞ ወደ ኋላው ተመለሰ ። ሆአአ ዳ. ፎንሴካም ፣ ፍራንሲስኮ ቬል

(1) የፖርቱጋሎቹ ዠግንነት ምዕ. 18 ገጽ 56

ሆም እንደዚሁ በጀግንነት እየተዋጉ በግራኝ ጦር ላይ ጉዳት ካደረሱ በኋላ እየተመቱ ወደቁ ።

ክርስቶፎሮስ አራቱ የጦር አለቆቹና ከጭፍሮቹ የሚበልጡት ስለተገደሉበት የርሱም ቁስል ስለጸናበት ወደ ኋላ ተመልሶ ሲከላከል በዚሁ ጊዜ ጳጳሱ (ቤርሙዴዝ) በበቅሎ ወደኋላ መሸሹን ንግሥቲቱም እንደዚሁ ወደ ኋላቸው ለመመለስ ሲያስቡ ፖርቱጋሎቹ አብረው ወደ ኋላ እንዳይሸሹ ሲል ንግሥቲቱን እየጠበቀ ለማቆየት ከመፈተን ጋር ራሱም እስከመጨረሻ እዚሁ ተዋግቶ ለመሞት ቆርጦ እንደነበረ ካስታንሆሶ በዚሁ ምዕራፍ ላይ አብራርቶ ያረጋግጣል ።

ዳሩ ግን ጭፍሮቹ አጠገቡ ያለው የተረፈ ትንሽ ወታደር በምንም ዓይነት ለመከላከል እንደማይችል የቁስለኛውንና የሟቹን ብዛት ከማሳየት ጋር እያስረዱ እንዲመለስ ስለለመኑት እሺ ብሎ ከበቅሎ ላይ እውጥተውት በአቅራቢያ ወደሚገኘው ተራራ ሽሽቱ ተዠመረ ። በበላይ ሆነው በስማቸው የሚያዋጉት ንግሥት ሰብለ ወንጌል የነርሱን ይኸን አሳዛኝ ዕድል ለመካፈል እስከ መጨረሻው ቆይተው በዚህ ጊዜ ሁሉም በየፊናው በሚሸሽበት ጊዜ ክርስቶፎሮስ ከማይለዩት ከ፲፬ ወታደሮች ጋር ሲጓዝ ንግሥቲቱ በብዙ ሠራዊት እንደታጀቡ በሌላ አቅጣጫ እንደሄዱ በዚህ ጊዜም እስላሞቹ እየተከታተሉ በደንጊያና በቀስት ብዙ ሰው እንደፈጁ ይገልጻል ።

ISIC

ከዚህ አያይዞ እስላሞቹ ወደ ሠፈራቸው ገብተው ምርኮውን ሲሰበስቡ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ወደ ነበሩበት ቤት ገብተው ከቁስላቸው ብዛት የተነሣ የማይንቀሳቀሱ ከ፵ የሚበልጡ ቁስለኞች እንዳገኙና እነርሱን ሲበረብሯቸው ይኸንኑ ይመለከት የነበረ አንድ የፖርቱጋል ቁስለኛ እንደ ሶምሶን "ነፍሴ ከነርሱ ጋር አብራ ትውጣ" ብሎ በአጠገቡ የነበረውን የተቀመጠውን ባሩድ ቀስ ብሎ ተንፏቆ ሄዶ ከሩን እያይዞ ባሩዱን እንዳፈነዳው ከዚህም ቤት አንድም ሰው በሕይወቱ እንዳልወጣ ያረጋግጣል (1) ።

በበኩላቸው ዮሐንስ ቤርሙዴዝና ጀምስ ብሩስ ስለባሩዱ ማፈንዳት ጉዳይ የተለየ አተራረክ ያቀርባሉ ። ዮሐንስ ቤርሙዴዝ «አንዲት ጻድቅ ሴት ወይዘሮ የንግሥቲቱ ሞግዚት የነበረች ሁለት ልጆችዋን እንደያዘች በእስላሞቹ እጅ ከምንወድቅ ብላ ባሩድ ያለበትን በርሜል በፈቃድዋ እሳት ለኩሳ አፈንድታ ከነልጆቿ ሞተች» ያለውን ጀምስ ብሩስ ደግሞ «ከድሉ በኋላ እስላሞቹ የፖርቱጋሎቹን ሠፈር በወረሩ ጊዜ ያገኙትን ቁስለኛ ሁሉ አረዱት ። በዚህ ጊዜ ሴቶቹ ተሸብረው ወደ ክርስቶፎሮስ ድንኳን እየሸሹ ቢገቡ ቱርኮቹ እነሱን ፍለጋ ተከታትለው ገብተው እንዳልሆነ በማጉላላት አስነወሩዋቸው ። በዚያን ጊዜ አንዲት ከታላቅ ቤተ ሰብ የምትወለድ አንዱን የፖርቱጋል ወታደር አግብታ የነበረች ኢትዮጵያዊት የሚደርስባትን አሰቃቂ ነውር በመመልከት እዚያ በነበረው የቤርሜል ባሩድ ላይ እሳት ለቃ ራሷን ወገኖቿንና ጠላቶቿን ጭምር ገደለች» የሚል ጽፏል ።

(1) የፖርቱጋል ጀግንነት ምዕ. 18

ምናልባት የፖርቱጋሉ ወታደር በንግሥቲቱ ሠፈር ለብቻው ሲያቃጥል ፣ ይኸኛውን ጸድቋ ሴት ወይም ከታላቅ ወገን የተወለደችው በክርስቶፎሮስ ድንኳን ውስጥ እቃጥላ ይሆናል ። ምናልባት አንዷ ያቃጠለችውን ሁለቱ ተራኪዎች ሁለት ሴት በማስመሰል ተርከውት ይሆናል (1) ።

በዚህ አሳዛኝ ጦርነት ላይ ስለ አዝማመሩና ስለ አፈጻጸሙ ስለነበረው ያመራር ጉድለት ምንም ዓይነት ሐተታ ሊቀርብ አይችልም ። ከመዠመሪያው ላይ የአምባ ሠንይትን ድል እንዳገኙ ንጉሡ ወዳሉበት ወደ ስሜን አቅጣጫ ቢሔዱ ይሻል ነበር እንዳይባል በዚህ ጊዜ ግራኝ የነበረው እንደታሪክ ነገሥቱ አነጋገር ደረስጌ ስለሆነ ወደርሱው ፊት ለፊት መሄዳቸው ስለሆነ መጋጠማቸው ሲጋጠሙም በዚያ ላይ ማን እንደሚያሸንፍ አይታወቅም ። ሰሀርት ላይ "እንደ ታሪክ ነገሥቱ አነጻ — እንዳመሆኔ" ተዋግተው ያሸነፉት እነርሱ ሥፍራ ይዘው ተከላካይ በመሆን እርሱ ከውጭ ወጊ በመሆኑ ይሆናል ። በዚህም ላይ ከጦርነቱ አስቀድሞ ደጋግማ በእርግጥ ከግራኝ ከመጋጠሙ በፊት ከንጉሡ ጋር ለመገናኘትና በርሳቸው መሪነት ተባብሮ ጦርነቱን መቀጠሉ ጠቃሚ መሆኑን በመረዳት ስሜን ድረስ ከፈላሻው ጋር በስውር ሄዶ አደጋ ጥሎ ወታደር ከወታደር ሲማታ እርሱ ከመሪው ከሲዲ መሐመድ ጋር ብቻ ለብቻ የተዋጋበት ምክንያት ሁሉ ግራኝ ሆነ ብሎ ንጉሡና ፖርቱጋሎቹ ሊገናኙበት የሚችሉበትንና ያስጠበቀውን በር ጥሶ ነፃ ለማድረግ ነው ።

ISIC

በዚህ ጊዜ ደግሞ ንጉሡ በትክክል ወዴት እንደነበሩ አይታወቅም ከሸዋ ነስረዲንን አሸንፈው ወደ ስሜን መመለሳቸውንና ወዲያው ፈረንጆቹ መምጣታቸውን ለመግለጽ ታሪክ ነገሥቱ ንጉሡ ወደ ስሜን ምድር ሄዱ በዚህ ዘመን ፈረንጆች መጡ ብሎ ነው ያለፈው ። በይፋት ያደረጉትን ወሬ ግራኝ ሰምቶ ግራኝ ራሱ ወይም የግራኝ ጦር ከፉኛ ስለተከታተላቸው በግሥጋሤ የግራኝ ጦር በፍጹም ሊደርስባት ወደ ማይችለው ሥፍራ ምናልባትም ወደ ምዕራቡ ክፍል ወደ ለማልሞ ሄደው በዚያ እንዳሉ ወይም እንደተባለው ከዓባይ ደቡብ በሚገኘው በጋፋት እንደ ሆኑ አይታወቅም ። በዚህም ላይ ክርስቶፎሮስ በፊት ፈላሻ (ይሁዲ) በኋላ ክርስቲያን ሆነ ከተባለው ሰውዬ ጠይቆ እንደተረዳው ከንጉሡ ጋር ያለው ጦር ትንሽ ነው በዚህ ላይ ያሉበት ሩቅ ስለሆነ ለጊዜው ከርሳቸው ጋር በቶሎ ለመገናኘት የጊዜው ማጠር እንዳላስቻለው ተገንዝበናል ። ይኸውም ሆኖ እርሱም ንግሥት ሰብለ ወንጌልም ከንጉሡ ጋር ከተገናኙ በኋላና ግራኝ አዲስ ርዳታ ካገኘ ወዲህ ቢዋጉ አሸናፊው አይታወቅም ።

ደግሞ እርሱ ስሜን ከንጉሡ ለመገናኘት ሲል ብዙ ቀን መሰንበት ቀርቶ የአንድ የሁለት ቀን ጊዜ አጥፍቶ ቢሆን ኖሮ ወልፋ ንግሥቲቱና ፖርቱጋሎቹ ያሉበት ሠፈር እርሱ በሌለበት በግራኝ ተወግቶ ቢሆን አሁን ከተደረገው የበለጠ ጥፋት በሆነ ንግሥቲቱና እነ ቤርሙዴዝም የምርኮ አደጋ ሊደርስባቸው በቻለ

(1) Voyage J. Bruce. ገጽ 202

ነበር ። የሆነ ሆኖ አሁንም የደረሰው ጥፋትና እልቂት በቀላሉ የሚታሰብ አይደ ለም ። በሰሀርት ግራኝን አቁስሎ እንዲሸሽ ያስገደደው ጊዜ ወዲያው እረፍት ሳይ ሰጥ አባሮ መጨረስ ይገባው ነበር እንዳንል ለመከታተል ደጋግሞ መሞከሩን በዚ ሁም ከኡመር ጋር መዋጋቱን እንብበናል ። እስከ መጨረሻ ማባረሩ ለሩቅ ተመል ካች ቀላል ይመስላል እንጂ ብዙ ጓዝና ስንቅ ለያዘ ታላቅ ጦር ፤ ቁስለኛና የሞተ ለበ ረከተበት በጉዞና በጦር ለደከመ በዚህም ላይ የሸሸበት አቅጣጫ ዞቡል የደንከል በረሃማ አገር ስለሆነ የዚህ ሁሉ አፈጻጸም ግራ አግቢ ነው ።

እነሆ በአሁኑ ጦርነት እንኳን ግራኝ ይኸን ያህል የቱርክና የዓረብ ያገር ተወ ላጅ ብዙም የፈረሰኛ ጦር እያለው ምንም እንኳን አንዳንዶቹ በራሪዎቹን ቢከታተ ሉም የያዘውን ከማጽናት አልፎ የሸሹትን ራሱ ግራኝ አባሮ ሴቷን ንግሥት ሰብለ ወንጌልን እንኳን ሊማርክና የተረፈውንም በራሪ ጦር ፈጽሞ ለማጥፋት አልቻ ለም ። ይኸም ተርፎ የሸሸ ጦር በኋላ ካፄ ገላውዴዎስ ጋር ተገናኝቶ በማበር ግራ ኝን ከሞት ሲያደርስ ወደፊት እንመለከታለን ።

ካስታንሆዞ በሰሀርት ጦርነት መቶ ፈረሰኛ ቢኖረን ኖሮ ከግራኝ ጋር የጦር ነቱ ነገር ያንለት ያልቅ ነበር ሲል ምኞቱን በትንቢታዊ ቃል ሰንዝሯል ። ነገር ግን እንደዚህ ያለውን አስተሳሰብ ለማመን ችግር ነው ። በሰሀርት ጦርነት ሽሽትን የፈ ጠረ ዋናው ምክንያት የግራኝ መቁሰል እንጂ ጦር ሠራዊቱ ፈረሰኛው አልቆ እዚያ የነበሩት ቱርኮች ሁሉም ሞተው ወይም ቆስለው አይደለም ። ስለዚህ መቶ ፈረሰኛ ብቻውን ቢከተል ባንድ ወገን የቁጥሩን ማነስ ዓይተው ባንድ ወገን ደግሞ እንደ ዚህ ጨክነው ከአባረሩንና መሞታችን ካልቀረ እየሸሸን ከጀርባችን እየተመታን ከምንሞት ፊታችንን መልሰን በወንድነት እየተዋጋን እንሙት የሚል ቁርጠኛ አሳብ ይመጣል ። በዚያን ጊዜ ድል ለአባራሪ ለመቶ ፈረሰኛው ወይም ለበራሪው ለጅምላ ጦር መሆኑን በቅድሚያ ማወቅ አይቻልም ።

ISIC

በዚህ መካከል ደግሞ በክርስቶፎሮስ ደጋማ ላይ የነበረው ችግር ይዞ የመ ጣው የወታደርና የመሣሪያ ቁጥር የተወሰነ ከመሆኑ የተነሣ ባንድነት እየሆኑ ከመ መከት በቀር እየከፋፈለ በተያዘውና ባመነው አውራጃ ላይ ግማሹን እያስቀረ የቀረ ውን አስከትሎ ያልተያዘ አውራጃ ለመያዝ ወደፊት ለመቅደምና ጠላቱን እስከ ሩቅ ድረስ ለማባረር አያወላዳውም ።

ሌላም ሰው ንግሥቲቱም ይኸን ሠፈር ለቀን ንጉሡ ወዳሉበት እንሂድ የሚል ምክር ባቀረቡለት ቁጥር ደጋማ አገሩን ትተን ስንሄድ ከኋላ ይወጉናል ፤ ባገሩ የግ ራኝ ሰው ይገባበታል ። ሕዝቡም ግራኝን ፈርተን የሸሸን እየመሰለው እህል ውኃ ማቀበሉን ያቋርጣል የሚል ሥጋት እንደነበረበት ካስታንሆዞ በመጽሐፉ ላይ ብዙ ጊዜ ያወሳው ሁሉ በቂ ምክንያት ነው ።

በአገሪቱ ላይ የግራኝ ግዛት ከ፲፭ ዓመት ዠምሮ ስለጸና የግራኝም የአሸናፊ ነቱ ዝና እንደተረት ያህል ባገር ላይ ስለተመሠረተ በዚህ ባንድ ጭብጥ የፈረንጅ ጦር ርዳታ አይሸነፍም የሚል ግምት በየሰዉ ልብ ስለማይጠፋ አንዳንዱ እንደ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ካለው ቆርጦ ከገባውና ከተከተላቸው በቀር የቀረው "ዓይተ

ነው ጊዜ ወደሚያደላው" በሚል የውልውል መንፈስ ውስጥ ሳይገኝ አይቀርም ። ይሁን እንጂ በማናቸውም ረገድ የይሉኝታን የክብርን ጉዳይ ወደጐን አድርጎ ከመቶ ሰው ጋር ብቻውን ወደ ስሜን ሄዶ በመመለስ ፈንታ እንዳለ ንግሥት ሰብለ ወንጌልንና ጦሩን በሙሉ ጠቅሎ ወደ ስሜን በግሥጋሤ ቢሄድና ከንጉሡ ካፄ ገላ ውዴዎስ ቢገናኝ ኖሮ ምናልባት ከዚህ ዓይነቱ መሸነፍ መማረክና መሞት ለመዳን ይችል እንደሆነ በትክክል አይታወቅም ። ዳሩ ግን በስህርት ያሸነፈው ግራኝ አህ መድ በምሥጢር አዳዲስ የጦር መሣሪያና የቱርክ ወታደር ማምጣቱን ክርስቶፎ ሮስ የተረዳው ጦርነቱ ተገርምሮ በተፋፋመበት ሰዓት ስለሆነ የዠመረውን ውጊያ ከመቀጠል በቀር ሌላ የመውጫ ምርጫ አልነበረውም ።

የሆነ ሆኖ የዚህ የወፍላ ጦርነት በግራኝ አህመድ አሸናፊነት በፖርቱጋሎቹ ተሸናፊነት በዚህ ዓይነት ይፈጸማል ። ቤርሙዴዝ እንዳለው በቍጥር የሚያንሱ ፖርቱጋሎች በቍጥር ብዙ ጊዜ የሚበልጡዋቸውን የቱርኮቹንና የዓረቦችን ወታደ ሮች ፊት ለፊት በቀን ከመዋጋት ይልቅ ሹማምንቱ እንዳሉት በሌሊት አደጋ ጥለው ተዋግተው ቢሆን ኖሮ ያሸንፉ እንደነበረ አይታወቅም ። ቤርሙዴዝ ቱርኮቹ በሌ ሊት መዋጋት አለመቻላቸውንና በዚህም ላይ ሳይታጠቁ በሌሊት አደጋ ቢመቱ እንደሚሸነፉ እያስመሰለ የክርስቶፎሮስን ውሳኔና አመራሩን ዋጋ ቢስ በማድረግ የጻፈውን እንብበናል ።

ነገር ግን ፖርቱጋሎቹ የቻሉትን የሌሊቱ ውጊያ ቱርኮቹና ዓረቦቹ የማይችሉ በት ምንም ምክንያት የለም ። ሳይታጠቁ አደጋ ለመጣል ይቻል ነበር ተብሎ የሚ ሰነዘረውም ተስፋ ከንቱ ነው ። እንደ ግራኝ አህመድ ያለ ብልህ ጠርጣሪ ሊዋጋ ራሱ መጥቶ ከጠላት ሠፈር አጠገብ ሆኖ ሳለ ያለ ቃፊር እርሱም ወታደሩም ነቅ ተው ታጥቀው አይጠባበቁም ማለት ከንቱ ስለሆነ የቤርሙዴዝ አስተያየት የሚደ ገፍበት የክርስቶፎሮስ የአመራር ዘዴ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ።

## ምዕራፍ ፻፳፪

## የክርስቶፎሮስ ድጋሚ መማረክና መገደል (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም)

የጦርነቱን አዝማሚያ ሲያይ በጳጳስነት ስም የሚጠራው ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ንግ ሥት ሰብለ ወንጌልን ይዞ ለመሸሽ ሲሞክር ድጋሚ ደግሞ ንግሥቲቱ ከሄዱ ቆም የሚዋጋው ወታደር ተስፋ ቆርጦ ይሸሻል በማለት ንግሥቲቱን ማስጠበቁን ካስታ ጉሆ ጠቅሶታል ። መሸነፍን ፣ ሽሽትን የማይወደው ዠግናው ክርስቶፎሮስ ራሱም ክፉኛ ከሁለት ላይ ከቆሰለ ብዙ ወታደርም ካለቀበት በኋላ በሹማምንቱ ልመና ብቻ እሺ ብሎ ወደኋላ ማፈግፈግን ፈቅዶ ኃላፊነት አስገድዶት ትእዛዝ ሰጥቷል ።

የሽሽቱን ሁናቴ ቤርሙዴዝ እንደዚህ ሲል ይተርካል «ከሽሽት ቀደም ብሎ ዋናው ጦር ሳያልቅ ንግሥቲቱን ወደ ተራራ እንድንመለስ ብጠይቃት የሚቀመጡ

በት በቅሎ የሌላቸውን ከርሷ ጋር ያሉትን የሴት አመቤቶች ትቼ አልሄድም በማ ለት እምቢ ስላለች አስገዴጂ እሷና ከቀንጆዎቹ አሀቶቿ አንዲቱን በኔ ፊት ፊት እንዲሄዱ አደረግሁ ። አንዲቷን ልጅዋን በኔው ፈረስ ላይ አፈናጥጬ ጉዞው ተዠ መረ ።

ከንግሥቲቱ ጋር በተራራው ራቅ ብለን ሌሎቹ ሽሽዎች እንዲደርሱብን አረፍ አልን ። በተለይም መጠበቅ የፈለግነው ክርስቶፎሮስ ደጋማን ነው ። ንግሥቲቱም እኛም ሞቶ ይሆን ወይስ ተማርኮ ይሆን የሚል ጭንቀት ገብቶን ሳለ በዚሁ ጊዜ እጁን እንደ ቆሰለ ደርሶብን አገኘነው . . . . በዚህ ጊዜ ንግሥቲቱ የራሷን የሻሽ ቀጸላ ከራሷ ላይ ገፋ የሚያስቃየውን ቁስሉን ራሷ አሠረችለት ። እርሱ ግን ከቁ ስሉ ይበልጥ የተሰቃየው ስለ መሸነፋና የንጉሡ ሰንደቅ ዓላማ ስለመማረኩ ነበር ። ሰንደቅ ዓላማዬ ከሚማረክ እኔ ከጦርነቱ ላይ ብሞት ይሻለኝ ነበር አለ ። ከዚያ ሰው እንጂ ዋናው ሰንደቅ ዓላማ በተለይ በዚህ አገር ምንም አይደል ብዬ መከሬው . . . ጉዟችንን ያዝን ።

ስንጓዝ ባንድ ወንዝ ላይ ድልድይ መሳይ አግኝተን በዚያ ወንዙን ስንሻገር ክርስቶፎሮስ ከወንዝ ወዲህ አቀመጣለሁ እንጂ ወንዙን ተሻግሬ አልሄድም ብሎ የተሸከሙትን አሽከሮቹን አውርዱኝ አላቸውና አውርደው ባሊጋ ላይ አስተኙት . . . . . . አሽከሮቹን አልጋውን ተሸከማችሁ እንሂድ ብዬ ትእዛዝ ሰጥቼ ለማስነ ሣት ስሞክር ከዚህ ሥፍራ አልንቃንቅምና እምቢ ታልክ ራሴን ነው የምገድለው ስላለኝ ተውሁት ። እንግዲያው እኔም ካንተ ጋር ነው የምቀረው ብለው የለም ስሰ ዉም ላገሪቱም ታስፈልጋለህና ሂድ ብሎኝ . . . . . ትቼው ሄድሁ ። እርሱም ከአሽ ከሩና ከጸሐፊው ከሦስት ፖርቱጊዞች ጋር ወደ አቅራቢያው ዋሻ ሄደው ተደበቁ ።

ከዚያ ወደ ንግሥቲቱ ሄጄ ከፈረሷ ላይ እንድትወጣና ወንዙን ሌሊቱ ሳይነጋ በቶሎ እንድንሻገር ብለምናት እርሷም ክርስቶፎሮስን ትቼ አልሄድም አለች ። በዚ ያን ጊዜ ጠላት በቅርብ ስላለ በቶሎ ወንዙን ባንሻገር የርሷ ሕይወት ብቻ ሳይሆን የልጆቿም የመንግሥቷም ጥፋት እንደሚደርስ አስረዳኋት ። “በዚህ ቦታ ይህ ሰው ከሚቀር የገዛ ልጄ ቢቀር እመርጣለሁ” ብላ በለቅሶ እያማረረች በግድ ከፈረሷ ላይ (1) ወጣችና ወንዙን ተሻገርን ። ጕሕም ቀደደ ፤ በደረስንበት ተራራ ላይ ሆነን በሩቅ ቁልቁል ስንመለከት ክርስቶፎሮስን በተውንበት ቦታ እስላሞቹን አየናቸው ከዚያ እስላሞቹ እንዳይደርሱብን የምንችለውን ያህል እየተፋጠንን ቀኑን ሙሉ ወንዝና ተራራ በመሻገር በሙቀትና በድካም ስንጓዝ ዋልን ስንቅም አልቆ ከየዛፉ ቱምርና ቡና እየለቀምን ከየወንዙም ዓሣ እየያዝን . . . . . በላን በዚያን ጊዜ ያገኙ ገኘ ብዙ የሚበላ ስንቅ ይዞልን ስለመጣ ተነፈስን ። ሕይወታችንም ከደጋ እንዳመ ለጠ ቆጠርነው» (2) ።

(1) ቤርሙዴዝ በቅሎውንም ፈረስ የሚለው ይመስላል ።

(2) Histoire du christianisme ........................ ገጽ 140 ። በዚህ ላይ ቤርሙዴዝ ብዙ ወንዝ ተሻግረን ከወንዙ ዓሣ እየያዝን በላን የሚለው የሰቆጣና የአበርጋሌ ወንዝ አገሩም ላስታ ሳይሆን አይቀርም ። ከዚያም ወደ ስሜን ለመድረስ የተከዜን ወንዝ መሻገር አለባቸው ።

ይኸ ሁሉ ዝርዝር ታሪክ በካስታንሆዞ መጽሐፍ ውስጥ ይጐድላል ። ቢርሙዴዝ ባይኑ ያየውን የክርስቶፎሮስን እስከ ዋሻው መደበቅ ድረስ ይኸውም ማለት ትቶት እስከሄደበት ድረስ ያለውን ሲጽፍ ሽሽቱ በየፊናው ስለሆነ ምናልባት በሌላ መስመር የሸሸው ካስታንሆዞ የክርስቶፎሮስን የአመራረኩንና የአማሟቱን ዓይነት ከክርስቶፎሮስ ጋር አብሮ ተማርኮ በኋላ ካመለጠው ላይ እያጣራ ጽፎታል ማለት ነው ። በርሱም መጽሐፍ የሚነበበው ከዚህ በሚከተለው ዓይነት ነው ።

ከጦርነቱ ቦታ ሽሽት በተደረገ ጊዜ ክርስቶፎሮስና ጓደኞቹ ሌሊቱን በሚያሳዝን አኳኋን ሲጓዙ አድረው ትንሽ ለማረፍ ብለው ከመንገድ ወጣ ብለው ባንድ ጫካ ካለበት ሸለቆ ውስጥ ገቡ ። በቁስልና በጉዞ የደከመውን ደጋማን ጭፍሮቹ ከበቅሎ አውርደው ቁስሉን አጥበው የሚያደርጉት ቢቸግራቸው በቅሎውን አርደው በበቅሎ ሞራ የክርስቶፎሮስንና የራሳቸውን ቁስል ሲቀባቡ የነርሱን ዱካ እየተከታተሉ ያባርሩ ከነበሩት ውስጥ ፲፪ ቱርኮችና ፳ የሚሆኑ የእግረኛ ወታደሮች ማባረር ደክሟቸው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ በድንገት አንዲት አሮጊት ብቅ ብላ ታየቻቸው ። እስላሞቹም ወሬ ለመጠየቅ ብለው ወደርሷ ሲያመሩ እርሷ ግን መንገዷን ቀጥላ ሸለቆውን እያቋረጠች ዝም ብላ ስትሄድ እነርሱም ሲከተሏት እርሷ በቀጥታ ክርስቶፎሮስ አለበት ቦታ ስትደርስ እነርሱም ደርሰው በአለባበሱና በትጥቁ እርሱ መሆኑን አውቀው በደስታ ከነጓደኞቹ ማረኩት ። ወደ ግራኝም ሲወስዱት አይሁድ በክርስቶስ ላይ እንዳደረጉት ዓይነት ያን የመሰለ ዝግና ከማንገላታት ጋር እስላሞቹ እያላገጡ ዘበቱበት ።

እግራኝ ፊት የቀረበ ጊዜ ግራኝ የፖርቱጋሎቹን የተቆረጠ ብዙ ራስ ከፊቱ አስደርድሮ እስተ፡ እወቃቸው የማን ራሶች ናቸው እያለ አፌዘበት ። ቀጥሎም እነዚህ ካንተ ጋር ሆነው የያዝሁትን አገር ለማስለቀቅ የመጡ ናቸው እኮ እያለ እየቀለደ ልብሱን አውልቁና ሁለት እጁን የፊጥኝ አሥራችሁ ግረፉት ብሎ በሻንቅሎች ጫማ ፊቱን አስደበደበው ። ቀጥሎ ሪዙን በሰም አስቀብቶ በሳት እንዲያያዝ አድርጐ ያንን ከጦርነቱ በፊት የላከለትን መቀስ አስመጥቶ ያውልህ ማንም ሳይሠራበት አንተኑ ጠብቆሃል ብሎ ቅንድቡንና ሽፋሉን አስቆረጠው ። ከዚያ በኋላ እያዞራችሁ በየሠፈሩ ለሰዎቻችን አሳዩት ብሎ አዙረው አሳይተው ሲጨርሱ ወደርሱ ስው ድንኳን መልሰው አመጡትና ግራኝ ራሱ በመጥረቢያ ቆርጠ ገደለው ሲል ጸሐፊው ያረጋግጣል ። ካስታንሆዞ ይኸን የጻፈው ከደጋማ ጋር አብሮ ተማርኮ በኋላ ከግራኝ ሠፈር አምልጠ ከመጣው የፖርቱጋል ተወላጅ እየጠየቀ አስተካክሎ የነገረውን ነው (1) ። ይኸንንም አተራረክ ከዚያ ወዲህ የጻፉት እነቴሌስ ፣ እነ ጀምስ ብሩስ ያረጋግጣሉ (2) ።

ስለክርስቶፎሮስ ደጋማ መሸነፍና አሟሟት በበኩሉ ታሪክ ነገሥታችን ከዚህ በፊት የያፌት ልጅ የቶቤል ልጆች (ፈረንጆች) ከባሕር መጡ ። እነርሱም ውጊያ

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 19 ፤

(2) Historia geral de Etiopia-a alta ምዕ. XIV ገጽ 169 - 171

እንደ ተኩላ የጠማቸው ጦርነት እንደ አንበሳ የራባቸው ናቸው ብሎ በግዕዝ ከጠቀሰ በኋላ ከዚሁ አያይዞ እንደዚህ ይላል «ያስታወስናትን ቤተ ክርስቲያን (የክርስቲያን ሕዝብ) ለመርዳት መጥተው (ፖርቱጋሎች) እስላሞችን ማሸነፍ ዠምረው ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ አላደላቸው የመጨረሻ ድል ለመዝለቅ ሲሞክሩ ይማም አህመድ ተዋግቶ ብዙዎቹን ፈጃቸው ምርጡዎቹንም ማርኮ አሠራቸው ። ልቡ እንደ ብረትና እንደ ነሐስ የጸናውን አለቃቸውን (ክርስቶፎርስን) ፈሪና ደካማ ሰው እንደሚያደርገው ማርኮ ከያዘው በኋላ በማይገባ ዓይነት ገደለው» (1) ። ታሪከ ነገሥቱን ያዘጋጀው ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ እንዳለው በርግጥ ግራኝ በክርስቶፎሮስ ላይ የፈጸመው አሰቃቂ ስቃይ የፈሪዎችና የአብሪተኞች ሥራ ነው እንጂ የዠግኖች ሥራ አይደለም ። ጦርነቱን ዠምረው ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ለፖርቱጋሎቹ አልተሰጣቸውም ያለው በሚቀጥለው እንደሚነበበው ድሉን ወደ ፍጻሜ የማድረስ ዕድል ለገላውዴዎስ ብቻ ተሰጠ ለማለት ነው ። ይኸውም ከእውነት ያልዘለለ አባባል ነው ።

በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ ቱርኮች በደጋማ አገዳደል አልተስማሙም ኖር በቀጣ ወደ ግራኝ አህመድ ሄደው ይኸን በሱልጣናችን ዘንድ ሳይቀር ስሙ የታወቀውን ሰው ከነሕይወቱ በምርኮኝነት እንወስዳለን ብለን ስንመኝ ለምን ገደልኸው ብለው እየተናደዱ ወቅሰው በዚሁም አኩርፈው ለብቻቸው የተረፉትን ፖርቱጋሎች ይዘው ከግራኝ SIC ተለይተው እንደነበረ ከተማራኪዎቹ ፖርቱጊዞችም መካከል አንዱ አዘንግቶ ጠፍቶ ወደ ወገኖቹ ሄዶ መደባለቁን ይጽፍና በዚሁ ቅያሜ ላይ እንዳሉ ሁለቱ መቶ ቱርኮች በሞቱት ምትክ ከወገኖቻቸው ተለይተው ከግራኝ ጋር ተስማምተው ሲቀሩ የቀሩት ቱርኮች የክርስቶፎሮስን ጭንቅላትና የተማረኩትን ፲፪ ፖርቱጋሎች ይዘው በመርከብ ተሳፍረው ወደ መጡበት ወደ ዘቢድ (በርሱ አጻጻፍ አዝቢድ) ተመለሱ ሲል ይደመድማል (2) ። ዠሮም ሎቦ የሚባለው ሚሲዮናዊ ባዔ ፋሲል ጊዜ መጥቶ ከሽማግሌ እየጠየቀ የሚቹን ዓጽም መሰብሰቡን ፤ ደጋማ በተገደለበት ቦታ ጠበል መፍለቁን ከተረከበት ላይ ስለአሟሟቱ እንደዚህ ይላል «ክርስቶፎሮስ ደጋማ ተይዞ ከግራኝ ፊት በቀረበ ጊዜ የግራኝን አጐትና ዘመድ እንዲያክም ተጠይቆ "ከሕንድ የመጣሁት እነሱን ለማከም አይደለም" የሚል መልስ በኩራትና በንቀት የመለሰ ጊዜ ግራኝ ተናዶ ልብሱን አስገፍፎ ራቁቱን ሆኖ በራሱ የወፍጮ መጅ ተሸክሞ በየሠፈሩ እንዲዞር . . . . . እድርጎ በኋላም ራሱን ቆርጦ ወደ ዓረብ አገር እንደላከውና ዓረቦች ራሱን አራት ላይ ቆራርጠው እንደተከፋፈሉት ያመለክታል (3) ።

(1) እለ ረድእዋ ለቤተ ክርስቲያን ዘዝከርት ላእለ ፀብእ ተንባላት ወወጡኑ መዊዓ ። ሶበሰ ሐለዩ በጺሓኀበ ፍጻሜ መዊዕ ዘኢ.ተውህበ ሎሙ ፀብዖሙ ኢማም አህመድ ወቀተለ መብዝኅቶሙ ወአዕቀጸ ኅሩያኒሆሙ ወቀተሎ ለሊቆሙ ኃያል ወጽኑዕ ዘልቡ ከመ ሐፂን ወብርት በቀትል ዘኢይደሉ ሎቱ እምድኅረ እኀዞት ወተሞቅሖ ዘውእቱ መከፈልተ ድኩማን ወፅቡዓን . . . . . ታሪከ ነገሥት (የፓሪሱ) ገጽ 99 ። የገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ገጽ 16 - 17 ፤

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 19 ፤

(3) Voyage Historique d'Abissinie - J. LOBO ገጽ 92 - 93

ክርስቶፎሮስ ዳጋማ ቆስሎ ከተኛበት ጫካ እንደ አጋጣሚ ጠላቶቹን እየመ ራች ስለወሰደቻቸው ሴት ካስታንሆዞ ቢቸግረው ሰይጣን ነች ብሎአል ። ባንዳንድ መጽሐፍ ላይ ደግሞ ክርስቶፎሮስ ዳጋማ በወዳጅነት ይዟት የነበረች የቱርክ ሴት ነበረችና እሱን ከድታ የሔደበትን ዱካ በሩቁ ተከታትላ ለወገኖቿ አሳየቻቸው ያሉ አሉ ። ምትሀትም ነች ተብሏል ። እስላሞቹ ግን ክርስቶፎሮስ ያለበትን ለማመ ልከት ነቢዩ መሐመድ የላካት ናት ብለዋል ። ነገር ግን ይቺ ሴት ከዚህ በፊት በቤ ርሙዴዝ አጻጻፍ ላይ እንደተረዳነው በስሜን ክርስቶፎሮስ ከሲዲ መሐመድ ጋር ተዋግቶ ሚስቱን ከማረከ በኋላ ለራሱ ያደረጋት ሴት ለጊዜው በማታለል ክርስትና ተነሥታ እርሱን የወደደች መስላ በዚህ ጊዜ ክርሱ ዘወር ብላ ወደ ወገኖቿ ገብታ እየመራች እሲዛው ይሆናል ። የሆን ሆኖ በዚህ ዓይነት ሲዋጋ የቆሰለው ቆስሎ የተ ማረከው ተማርኮ አንገቱ በመጥረቢያ የተቆረጠው የክርስቶፎሮስ ዳጋማ የሕይ ወት ታሪክ በዚህ ዓይነት ይፈጸማል ።

ካስታንሆዞ የክርስቶፎሮስን ሥቃይና አሟሟት በዚህ ዓይነት ሲጽፈው አል ሄድም ቢለው አስገድዶ አሥንሥቶ በማስወሰድ ፈንታ እምቢ አለኝ ብሎ ትቶት የሄደው የክርስቶፎሮስን አመራር ባንዳንድ ቦታ የሚነቅፈው ቤርሙዴዝ ስለአሟ ሟቱም ከካስታንሆዞ የተለየ ታሪክ ያመጣል ። ከግራኝ ፊት ተይዞ እንደቀረበ እስ ላም ሁንና ልግርሀ ልሹምሀ ቢለው ክርስቶስን ክጄ ያንተ የውሸታምና የውሻ ሃይማኖት አልቀበልም ብሎ እምቢ ካለ በ1516 ብዙ ማባበል የሸሹት ፖርቱጊዞች የኢትዮጵያን ንጉሥ (ገላውዴዎስን ወይስ ሰብለ ወንጌልን ?) ትተው ወደ አገራ ቸው እንዲመለሱ ደብዳቤ ባንድ የፖርቱጋል ቋንቋ በሚያውቅ ስልብ ተቆጣጣሪ ነት አጽፎት እንደነበረ ሆኖም ዳጋማ በደብዳቤ ላይ አትመኑ በግድ ነው የጻፍሁት የሚል ምልክት (የእሾህ ?) አድርጎ እንደነበረና ይኸንኑ መርምረው ሲደርሱበት ፖርቱጋሎቹ ሁሉ መደሰታቸውን ይገልጻል (1) ።

የሆን ሆኖ ከዚህ በፊት እንዳወሳነው የክርስቶፎሮስ አባት ቫስኮ ዳጋማ በዓ ለም የታወቀ የፖርቱጋል መርከበኛ ሹም ሆኖ በደቡብ አፍሪካ በሞዛምቢክ ፣ በሞ ምባሳ ዞሮ ሕንድ በመግባት የመዠመሪያውን የባሕር መስመር እ. አው. ቀጥር በ፲፬፻፺፰ ዓ. ም. ላገሩ ለፖርቱጋልና ለዓለም የከፈተ ነው ። ሕንድ ደርሶ ወደ አገሩ በ፲፬፻፺፱ ዓ. ም. ከተመለሰ በኋላ በ፲፭፻፪ ዓ. ም. ፳፩ መርከቦች ይዞ እንደገና ወደ ሕንድ ተመልሶ ዞሞሪ የሚባለውን የኮቺን ንጉሥ በውጊያ አሸንፎ ከባሕር ጠረፍ በሚገኙት በካሺን ማላባር (ኬ ራለ) ላይ የፖርቱጋልን ገዥነት ስለመሠረተ በዚሁ የአገልግሎት ውለታ በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ በሕ ንድ ግዛት ላይ እንደራሴ አድርጎ ሾሞት ነበር ።

እሁንም ባለፈው እንዳነበብነው የቫስኮ ዳጋማ አንደኛው ልጁ የክርስቶፎ ሮስ ታላቅ ወንድም እስጢፋኖስ ዳጋማ የሕንድ የንጉሥ እንደራሴ በነበረበት ሰዓት ከሕንድ የጦር መርከብ ይዞ መጥቶ በስዌዝ በዘይላ ያሉትን የቱርክ የጦር

(1) Histoire du christ ................ ገጽ 114 - 145

መርከቦች በውጊያ አሸንፎ እነዚህን ፬፻ የሚሆኑ የፖርቱጋል ወታደሮች በፈቃዱ እኔ መሪ ሆኜ ልሂድ ብሎ የለመነውን ታናሽ ወንድሙን ክርስቶፎርስን ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ መላኩን እንብበናል ።

ስለዚህ ክርስቶፎሮስ ዶጋማ ታላላቅ የሙያ ተግባር ለመፈጸም አሳበ ጽኑ የሆነ የቤተሰብ ተወላጅ ነው ማለት ነው ። መቼም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በመሠረቱ የራሱን አገርና ንጉሥ ለማገልገል ፤ በዚሁ ክብርና ዝና በወገኖቹ ዘንድ ለማኘት መሆኑ የማይካድ ነው ። ከመጣ በኋላ በአምባ ሠነይትና በሰሀርት ከግራኝ ጦርና ከራሱ ከግራኝ አህመድ ጋር ተዋግቶ ከአሸነፈ በኋላ በመዠመሪያው ተግባሩ የፈጸመውን ጀብዱና ያስለቀቃቸውን አገሮች ለንጉሡና ለበላዩ ለሕንዱ እንደራሴ ማስታወቅ እንደነበረበት ያነበብነው ትዝ ሲለን በመሠረቱ ይህ ዠግና መኰንን የሚያገለግለው የአገሩን መንግሥት መሆኑ አይካድም ።

ሆኖም አገሩን ፖርቱጋልን ጥግና ዘመድ ያደረገው የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ሕዝብ በእስላሞቹ መጠቃት ዝርዝሩን ባይኑ ከአየው ከዮሐንስ ቤርሙዴዝ በሰማ ቍጥር ሁኔታው በኀዘን አናዶታል ። ይኸንንም ጥቃት ለመበቀል እኔው ራሴ ልሂድ ብሎ ወንድሙን መለመኑ ፤ ከመጣ በኋላ በግለት ጦርነቱን አጣድፎ መያዙ በዚሁ ምክንያት ነው ። ስለዚህ አድራጐቱ የክብርና የዝና ፍለጋ ብቻ ወይም ባጭሩ ለ[illegible]ማትና ለሹመት ሳይሆን ከልብ በፈለቀ ስሜት የተጠቃትን ለመርዳት ራሱን በፈቃዱ ለመሰዋት የቆረጠ የክርስቲያን መኰንን ነው ። በመዠመሪያ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል የተገናኘ ጊዜ እኔና እነዚህ የሚያዩዋቸው ፖርቱጋሎች ለክርስቲያን ሃይማኖትና አገሬቱን ለማዳን ስንል ለመሞት ዝግጁ ነን ያለውን እናስታውሳለን ።

ይህን የመሰለ ሰው ምንም እንኳን በሚያስደንቅ አኳኋን በርትቶ ቢዋጋ በወታደርና በመሣሪያ የብዛት ልዩነት ቢሸነፍም እንዲጋጣሚ ይሁን ወይም ባሏ ሲዲ መሐመድ እንደሞተ የወደደችው መስላ በኋላ በከዳችው ሴት ጠቋሚነት ተይዞ እየተደበደበ እየተተፋበት ከጠላቱ ፊት ቢቀርብም ሕይወቱ በሞት እስኪቆረጥ ድረስ የዠግናው የክርስቶፎሮስ ጠንካራ መንፈስ በጨካኙ በግራኝ አህመድ ፊት በፍጹም አልተሰበረም ።

ከዚህ በፊት ከመዠመሪያው ላይ ካነበብነው በቀር በአገሩ በፖርቱጋልና በሕንድ የሠራውን ዝርዝር ሞያ አናውቅም ። ነገር ግን ከሕንድ መጥቶ ምጥዋ ከደረሰበት ጊዜ ዠምሮ አሁን እንገቱን በመጥረቢያ ተቆርጦ ለመጣበት ዓላማ ሕይወቱን እስከሰዋበት ቀን ድረስ ያሳየው የአካልም የመንፈስም ብርታትና ጽናት ለትንግርት ነው ከማለት በቀር ሌላ በቂ ቋንቋ አይገኝም ። ቀብራራ ተድላና ደስታ ወዳድ ወይም ፈሪና አወላዋይ የጦር መኰንን አለመሆኑን የምንረዳው በትውልዱ በዘሩ የታላቅ ቤተ ሰብ ተወላጅ ሆኖ ሳለ በተድላ በደስታ ከሚኖርበት አገር መጥቶ ከፍ ያለውን የበላይነት ሹመት እንዲያዘ በጉዞ ላይ ዕቃ ተሸካሚ ፤ በጦርነት ሰዓት ከፊት ቀድሞ ተዋጊ ፤ ከሁለት ላይ ክፉኛ በቆሰለበት ሰዓት የቁስሉን ሕመም ጨክኖ በመያዝ በጋለው ጦርነት ውስጥ ወዲያና ወዲህ እያለ ራሱ ተዋጊ ተዋጊ

ውን አበርቺ ፤ ከሥቃይና ከመጥረቢያ በትር ፊት ከሚዛኑ የማይርቅ ደንበኛ የገርግና ምሳሌ ስለሆነ በመላው ዓለም ቢቀር በኢትዮጵያ ታሪክ ስሙ በግራኝ አህመድጉን በገናናነት ሊጠቀስ የሚገባው ሰው ነው ።

ሮመ ሮላንድ የሚባል የፈረንሣዊ ጸሐፊ ጀግና ማለት የሚቻለውን ሁሉ የሚያደርግ ነው ይላል ። ክርስቶፎሮስ ግን ሌላ ጀግና ሰው ከሚችለው በላይ ያደረገ ዠግና ይመስለኛል ። ያገራችን ታሪክ ነገሥት ፊሪዎች እንደሚያደርጉት በማይገባው እንጓደል ገደለው ሲል በግራኝ ላይ የሰነዘረበትን ፍርድ በግራኝ አጠገብ ያሉት ቱርኮች የተስማሙበት ይመስላል ። እነሱም ለምን ገደልኸው ብለው ግራኝን ተናደው በወቀሱት ጊዜ ከነሕይወቱ ወደ ጌታችን ወደ ቱርክ ሱልጣን እንወስደው ነበር ሲሉ ይኸ ስመ ጥሩ ዠግና እሥራት እንጂ ሞት አይገባውም በሚል ስሜት ሕይወቱን ለማዳን ያሰቡ ይመስላል ። ብዙውን የግራኝን የዠግንነት ሥራ ከዚህ በፊት በክርስቲኖቹ የጦር አለቆችና አሁንም በዚህ ወጣት ዠግና ላይ የፈጸመው ጭካኔ እንደሚያሳድፍበት የታወቀ ነው ።

ዳሩ ግን የበላይ አስተዳዳሪና የጦር መሪ ተከላካይም ቢሆን ወይም አጥቂ በሥራው ላይ ጭከናን ካልጨመረ በአስተዳደርና በአገዛዝ ውስጥ አብዛኛ ጊዜ በርኅራኄ የሚከናወን ነገር እንደሌለ አይዘነጋንም ። ራሱ ክርስቶፎሮስ በደባርዋ ሰፈር ላይ ክርስቲያን መስለው ሲሰልሉ የተገኙትን ISIC በሠረገላ አሳስሮ እንዳስበጣጠሳቸው እንገበበናል ። ይኸም ራሱ ጭካኔ ነው ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ፊትለፊት ሲዋጋ ቆስሎ የተማረከውን ዠግና የጦር አለቃ ቢጨክን ሊገድለው ቢራራ እሥሮ ሊያስቀምጠው የሚችለውን ከርኅራኄው ጭካኔው አመዝኖ በመጥረቢያ አንገቱን ቆርጠ መግደሉ ካልቀረ ከዚያ በፊት ያለው በጫማ ማስደብደቡ መጅ አስጭኖ በየሠፈር ማዞሩ ለምን ተጨመረ ሲያሰኝ መልሱ የአብሪተኝነት ፍሬ ብቻ ነው ማለት ይቻላል ።

ቤርሙዴዝ በሌላ ቀን ወሬ እየጠየቀ የተረዳውን የክርስቶፎሮስን ፍጻሜ በበኩሉ እንደዚህ ሲል አተራረኩን ይፈጽማል «በክርስቶፎሮስ እግር የተሾመው አልፎንስ ጋልዱይራ በግራኝ ስም ክርስቶፎሮስ ደጋግሞ ለጻፈው ደብዳቤ ግራኝ ወደ አገራችሁ በሰላም ሂዱ ብሎ ለነበረው ስለመልካም ፈቃዱ አመስግኖ ቀጥሎ ግን እኛ እንደዠመርነው ግራኝ አህመድን ማርከን ወይም ገድለን የፖርቱጋል ንጉሥን ፈቃድ በመከተል አገሪቱን ነፃ ሳናወጣ ወደ አገራችን እንመለስም ብሎ ጽፎለት የነበረውን ክርስቶፎሮስ ተቀብሎ ለግራኝ ሰጠው ግራኝም በመልሱ ተናዶ ሳለ ወዲያው ከቁስልህ እንደምን ዳንህ ብሎ ክርስቶፎሮስን ቢጠይቀው መድኃኒት አቀማመም ስለማውቅ ነው አለው ። በዚያን ጊዜ የግራኝ አንድ ዋና የጦር አለቃ ቆስሎ ነበርና ያንን አከመው ብሎት አከመው ። አለቅየው ግን በታከመ በ፫ኛው ቀን ስለሞተ ተናዶ ክርስቶፎሮስን አስደበደበው . . . . . ቀጥሎም ራሱን ተቆርጦ ከተገደለ በኋላ ጭንቅላቱ ወደ ካይሮ ለዋናው አገረ ገዥ ተላከ ። የቀሩትም አባሎቹ

ወደ ይሁዳ (1) ወደ እደን ወደ ዘቢድ ተላኩ ። የተረፈውን አካሉን በሌላ ጊዜ በአቶራቢያ የሚገኙት የሃይማኖት ሰዎች (መነኰሳት) አንሥተው እንደ አንድ ጻድቅ አክብረው ቀበሩት ። እንገቱ በተቆረጠበት ቦታ አንድ ዕውራንን የሚያበራ ሕመማንን የሚፈውስ ጠበል እግዚአብሔር ስለ አፈለቀ የክርስቶፎሮስን እግዚአምላክ እንደወደደው ነፍሱንም እንደተቀበላት ገለጸ» (2) ።

ቤርሙዴዝ በዚህ ረገድ ከካስታንሆዞና ከንዝርሮም ሎቦ በመለየት የክርስቶፎሮስን ፍጻሜ በዚህ ዓይነት አወላዋይ ሁኔታ በመጠኑ አጉድፎ በዝርዝር ሲያመሌሎች ጸሐፊዎች ከየፖርቱጋሎቹ ጽሑፍ ላይ እሚልተው በማያወላውል ቆራጥነት በጦርነት ላይ የቀሰሉትን የግራኝን አጐትና የወንድሙን ልጅ እንዲያበቃ ተጠይቆ እምቢ ማለቱ ፤ ወገኖችህ የሸሹበትን አሳየን ተብሎ እሻፈረኝ ማለቱ ግራኝ ወደርሱ ጠጋ ብሎ እንግዲያው እስላም ሁንና ልማርህ ቢለው ተናዶ ከራቱ ላይ እንደተፋበት ከሌላው የዝግንነት አሟሟቱ ጋር ከጻፉ በኋላ ራስ መቆረጥየመጣው ከዚህ ድረቅ እምቢታ በኋላ መሆኑን ስለሚገልጹ ዞሮ ዞሮ በማናቸውም ረገድ ቢሆን ክርስቶፎሮስ ደጋግ አሟሟቱን አሳምሮ ስለ ኢትዮጵያ ደኅንነት ስለእንገሩ ክብር የተሠዋ ዝግና መሆኑን እምነን ወደሌላው ታሪክ እንተላለፍ ።

ISIC

## ምዕራፍ ፻፳፫

## የተረፉት ፖርቱጋሎችና ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከዔ ገላውዴዎስ ጋር በስሜን እንደተገናኙ (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ጥቅምት)

ከወልፋ ጦርነትና መሸነፍ በኋላ ከዚሁ ከወልፋ ንጉሡ ወደ እሉበት ወደ ስሜን አቶጣጫ ለመድረስ ወደ ላስታ ሲጓዙ ያን ከመሰለ ጦርነትና እልቂት በኋላ ጓዝን ቁስለኛን ይዞ ከኋላ የአሸናፊ አባራሪ በፈረስ እያዋከበ ሲያሳድድ የነበረውን ችግር ለመረዳት ቀላል ነው ። በዚህ መካከል «እርሱ ቆስሎ ከሚቀር ምነው ልጁ በቀረብለው በመራራ ኀዘን ንግሥቲቱ ጥለውት የሄዱት የዚያ የጉበዝ ክፉኛ ቆስሎከዚሁ እልሄድም ብሎ እምቢ ማለት የእብዛኛ ሹማምንት በጦርነቱ ላይ መውደቅየሚያመጣው የሞራል በትር ከፍ ያለ ነው ። ይኸን በመሰለው መሸነፍና በተዝረከረከ ሽሽት መካከል በንግሥቲቱም በቤርሙዴዝም አሳብ ጦርነቱን ተቀብሎ በመናር ባጠም ፈንታ ይኸን ጊዜ ወደ ስሜን ሄደን ንጉሡን ይዘን ተዋግተን ቢሆን ኖሮ ይኸ ሁሉ ሊደርስብን ባልቻለ የሚል ጸጸት ይኖራል ። ይኸን ጸጸት የቀሩትም ፖር

(1) ይሁዳ በዚህ ጊዜ በቱርክ ውስጥ የሚገዛውን ፓለስቲንን ይሁን ወይስ በደቡብ ዓረብ የሚገኘውን የአይሁድን ማኅበር ይሁን አይታወቅም ።

(2) Histoire du christ ........ ገጽ 144 - 148 ። Historia geral B. TELLES ምዕ. XIV ።

[illegible] ኛ ... ነት ገጽ 61 ።

ቱጊዞች ሳይካፈሉት አይቀሩም ። ነገር ግን ዠግንነትና ሂሳብ እኩል አይሄዱም ። የመሣሪያንና የወታደርን የቁጥር ብዛት ተማምኖ መዋጋት ራሱ ዠግንነት አይባልም ። ዠግና የሚባለው በቁጥር ያነሰ ጦር ይዞ በቁጥር የሚበልጠውን ተዋግቶ በማሸነፍ ዠብዱ የሚያሳየው ነው ። ሳይሆንለት ቀረ እንጂ ዴጋማ ለማሳየት ፈልጎ የነበረው ይኸንን ነበር ። ቢሸነፍም ቢማረክም የዠግንነቱ ክብር አልተነካም ። በውጊያ ያሳየው ዠግንነት በምርኮና በሥቃይ ጊዜ አልተለየውም ።

ነገር ግን በወዲህ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ያለው የባለ ጠበንጃ ተዋጊ ቍጥር ከ፩፻ መጉደሉንና በግራኝ አህመድ ዘንድ ምርጥ ባለጠበንጃ ተዋጊ ፱፻ የቱርክ ወታደሮችና የዓረቦች አዲስ መምጣታቸውን ስናመዛዝነው ንጉሡ ነገሥቱም ራሳቸው መሪ ሆነው ቢያዋጉ ኖሮ ድሉን ያገኙ ነበር ብሎ ማረጋገጥ አይቻልም ። በዚህም ላይ የአምባ ሠነይትንና የሰሀርቱን ድል አድራጊነት የቀመሰውና የጣመው ወጣቱ ክርስቶፎሮስ ዴጋማ በአሳቡ ውስጥ ያለ ዓፄ ገላውዴዎስ ኢትዮጵያን ከ፲፫ ዓመታት ዠምሮ እየቆላ ያመሳትን ግራኝ አህመድን በርሱ መሪነት ማርኮ ወይም ገድሎ የድል አድራጊነትን ክብርና ዝና ለግሉ ለመጐናጸፍ ውስጠ ምኞት እንዳለው እናውቃም ። ዓፄ ገላውዴዎስ በተረፈው ጦር በኋላ ግራኝን ለማሸነፍ የቻሉት በበኩላቸው በዠግንነት ተዋጊ የሆኑት የቱርክ ወታደሮች አብዛኞቹ ወደ መጡበት ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ መሆኑን ወደፊት እናነባለን ።

የሆነ ሆኖ ባለፈው ካነበብነው ከቢርሙዴዝ አጻጻፍ በመጠኑ ለየት አድርጐ በርሱ በኩል ያየውንና የሰማውን እየጨመረ የሽሽቱን ሁኔታና ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር የተደረገውን ግንኙነት ጸሐፊነትንና ወታISICነትን ደርቦ የያዘው በዚሁ ጦርነት የመቁሰል አደጋ የደረሰበት ካስታንሆሶ ከዚህ እንደሚከተለው ይጽፋል ።

«የመሸነፉለት ፖርቱጋሎቹና ክርስቲያኖቹ ኢትዮጵያውያን በምሽቱም በሌሊቱም ሲሸሹ እስላሞቹ በእግርና በፈረስ እየተከታተሉ ደክም ብሎ ወደ ኋላ የቀረውን ሲማርኩ ሲገድሉ አደሩ ። የማባረሩ ጉዳይ በማግሥቱም አልበረደም ነበርና አንድ ክፍል የእግረኛ ጦር ሲያባርር ከነርሱ ፊት ለፊት ደግሞ ሁለት የእስላም ፈረሰኞች እየጋለቡ በጣም ቆስለው ወደሚራመዱት ፖርቱጊዞች ሲደርሱ ሲሉ ሁለት ቁስል ያልጸናባቸው ፖርቱጋሎች ፈርናአ ካርዶዞና ሎፖ ዲ አልማንዛ የሚባሉት አዩዋቸውና በምን አኳኋን ከነዚህ አባራሪ ፈረሰኞች ወገኖቻቸውን ለማዳን እንደሚችሉ እያሰላሰሉ ወገኖቻቸውን በተቻላችሁ ወደፊት ሩጡ ብለው እነርሱ ወደ ፈረሰኞቹ ፊታቸውን አዙረው "ቅድስት ማርያም ሆይ ጠላቶቻችን መሣሪያችንን እንደያዝን ይግደሉን" ብለው ጸልየው ወደ እስላሞቹ ጠጋ ብለው ከሁለት አንዳቸው አልማንዛ ቋንቋቸውን ትንሽ ያውቅ ነበርና እንግዲህ ተማርከናልና መሣሪያችንን ግፈፉን አላቸው ። እነዚያም እውነት መስሏቸው ዘንጋ ብለው ለመማረክ ጠጋ ሲሉ እነዚህ ሁለቱንም መትተው ባንድ ጊዜ ጣሏቸው ። አንደኛው በመገርመሪያው በትር ወዲያው ሲሞት ሁለተኛው ቆስሎ ወደቀ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ፈረሶቻቸው ዝም ብለው ቆመው ነበርና ሁለቱ ፖርቱጋሎች በፈረሶቹ ላይ ተጋብተው ሊያባርር የመጣውን ከኋላ የነበረውን የእግረኛ ጦር ለማ

ባረር የመጡ አስመስለው ትንሽ ከአስደነበሯዋቸው በኋላ ወደ ወገኖቻቸው ፊታቸ ውን አዙረው በግልቢያ ደርሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገርዋቸው ሁሉም በነርሱ እየተ ገረመ ጉዞውን ቀጠለ» (1) ።

የፖርቱጋሉ ጸሐፊ ከዚህ አያይዞ ክርስቶፎሮስ ደጋማ ቆስሎ ባንደኛው ክፍል መሄዱን እንጂ ከሜካ ውስጥ ተማርኮ ወደ ግራኝ መሄዱ ስለአልተሰማ በየሠፈሩ ባደሩ ቍጥር በየሜካው በየመንገዱ ሰው እየላኩ ንግሥቲቱ ሲያስፈልጉ መሰንበታ ቸውን በጉዞም ላይ ፴ ፖርቱጋሎች ከጦርነቱ ላይ ያልዋሉ መጥተው (2) በወገኖቻ ቸው ላይ የደረሰውን ይኸን የጦር አደጋ በማየታቸው በተለይም የክርስቶፎሮስ ወሬ በመጥፋቱ በመካከላቸው ታላቅ ለቅሶ ከተነሣ በኋላ በተለይ ደግሞ ከግራኝ ሠፈር አምልጦ የመጣው የፖርቱጋል ተወላጅ በክርስቶፎሮስ ላይ የደረሰውን የሥ ቃዩን የአሟሟቱን እውነተኛ ወሬ በተናገረ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከነገሪዶ ቻቸው እንደ ልጃቸው ያህል ማልቀሳቸውንና ከዚያ ንግሥቲቱ ፍሬ ባለው አነጋ ገር ሁሉንም አጽናንተው ሲጨርሱ ወደ ሰሜን ጉዞው እንደ ቀጠለ ያመለክታል ።

በዚህ አጻጻፍ ካስታንሆዞ ከቤርሙዴዝ ይለያያል ። ቤርሙዴዝ ክርስቶፎሮስ ወንዝ ተሻግሬ አልሄድም ብሎ በፈቃዱ መቅረቱን በኋላም ተይዞ ወደ ግራኝ ዘንድ በቀረበ ጊዜ በግራኝ ትእዛዝ የቀሩት ፖርቱጋሎች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የሚል ጽፎ ነበር የሚለውን ሁሉ ካስታንሆዞ በፍጹም አያነሣም ። መቼም በክርስ ቶፎሮስ ደጋማና በ[illegible]ዴዝ መካከል በሥልጣን ሺሚያ ስምምነት ያልነበረ ይመስላል ። ካስታንሆዞ በሙሉ አጻጻፍ ክርስቶፎሮስን ስለአመራሩ ስለአሟሟቱ እያደነቀ ሲጽፍ ቤርሙዴዝ እየነቀፈ እያቀዘቀዘ ራሱ የሚከበርበትን ይኸን አደረ ግሁ ይኸን መከርሁ ይኸን አዘዝሁ እያለ ይጽፋል ።

በተለይ ደግሞ ከመዠመሪያው ላይ እንደተገነዘብነው ቤርሙዴዝ ይኸን የጻ ፈው ከኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ብዙ ዘመን ቆይቶ በ፲፭፻፶፭ ዓ. ም. (እንደ አው. ቈ.) በንጉሡ ትእዛዝ በራፖር መልክ ስለሆነ በአጻጻፉ ስለማናቸውንም ነገር የራ ሱን መከበሪያና መከላከያ ስለሚያበዛ ያለው ሁሉ አብዛኛው እውነት ቢሆንም ባንዳ ንድ ቦታ ሳያውቅ በስሕተት እያወቀም ለመከበሪያ ወይም ራሱን ከወቀሳ ውጭ ለማድረግ ሲል አንዳንድ ከእውነት የራቀ ቃል ስለሚጨምር በጠቅላላው ከርሱ ይልቅ የካስታንሆዞን ማመን የተሻለ ነው (3) ። ይኸም የብዙ ጸሐፊዎች አስተያ የት ነው ።

ፖርቱጋሎችና ንግሥት ሰብለ ወንጌል በጳጳስ ስም ከሚጠራው ወይም እንደ ጳጳስ ከሚከበረው ከዚሁ ከቤርሙዴዝ ጋር ከወፍላ (ከአሸንጌ) በላስታና በሰቆጣ በኩል አልፈው ከሰሜን ግዛት ሲገቡ ያገሩ ጌታ በደንብ እንዳስተናገዳቸው ካላታን

(1) የፖርቱጋሎች ዠማንነት ምዕ. 20 ፤

(2) ከምጥዋ ማለቱ ነው ።

(3) የፖርቱጋል ዠማንነት መግቢያ ገጽ 17 ፤

ሆኖ ያመለክታል ። ያገሩ ጌታ የሚለውም ከዚህ በፊት ክርስቶፎሮስ ዳጋማን እየ መራ የወሰደው ከሲዲ (ሰይድ) መሐመድ ጋር ያዋጋና የተዋጋ ወዲያውም ክርስት ናን ተቀብሎ አገሩን የተሾመውን ፈላሻውን መሆን አለበት ።

በስሜን ግዛት በገቡ በአሥረኛው ቀን ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ መጥተው እን ዳገኟቸው በደረሰባቸው ነገር ሁሉ በተለይ ደግሞ ሊያዩትና ሊገናኙት ይናፍቁት የነበረውን የክርስቶፎሮስን ሞት በሰሙ ጊዜ በጣም ማዘናቸውን ቀጥለው ፖርቱ ጋሎቹን ሁሉ ከልብ በማጽናናት አገራቱን (ኢትዮጵያን) እንደራሳቸው አገር እን ዲቆጥሩዋት እንጂ እንግድነት እንዳይሰማቸው አደራ ብለው የሐር ልብስና ሱሪ ሸልመው አንድ ድንኳን ለሁለት ሰው በተረፈ እልጋ ምንጣፍ ብርድ ልብስ በቅሎ ሌላም አስፈላጊያቸው የሆነውን ነገር እንዳደሉዋቸው ያመለክታል (1) ።

ቤርሙዴዝ በበኩሉ ስለ ዓፄ ገላውዴዎስ መምጣት ከናታቸውና ከፖርቱጊ ዞች ጋር መገናኘት ባጭሩ እንደዚህ ይላል «ገላውዴዎስ በ፶ ፈረሰኛ በባለብዙ በቅሎኞች ታጅበው ሲመጡ ሹማምንት ሁሉ የፖርቱጋሎችንና ያገሩን ሰዎች እስ ከትለው ከሠፈር ወጣ ብለው ተቀበሏቸው ። ከዚያ በነዚህ ሁሉ ታጅበው ወደኔ ድንኳን ሲመጡ እስከ በሩ ወጣ ብዬ ተቀበልሁዋቸው ። በአውሮፓ ከሮማ ጳጳስ ይልቅ በዚህ አገር ጳጳስ ስለሚከበር ወደበር ወጣ ብዬ መቀበሌን እንደ ክብር ቆጠ ሩት ። ከዚያ ወደ እናታቸው ድንኳን ሄደው ተገናኙ ። ከዚህ በኋላ በርሳቸው ትእ ዛዝ ስለሚቹ ስለክርስቶፎሮስ ዳጋማ ሞት የ፬፲፫ን ኀዘን ተደረገ» (2) ። የጀምስ ብሩስ አተራረክ ደግሞ እንደዚህ የሚል ነው «ገላውዴዎስ የክርስቶፎሮስ ዳጋማን ሞት ሲሰማ ታላቅ ኀዘን ተሰማው ሦስት ቀንም አለቀሰ ። ለፖርቱጋሎቹም ያካፈ ሉት ዘንድ ፫ሺ ወቄት ወርቅ ላከላቸው . . . . . እነሱም ወደርሱ በቶሎ መጥተው ከግራኝ ተዋግተው ያለቃቸውን ደም ለመበቀል አቻኩለው ለመኑት» (3) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ከዚህ በፊት እንደ አነበብነው መጠነኛ ጦር ይዘው ከትግሬ ስሜን ከስሜን ሸዋ ሄደው ብዙ ጊዜ ተዋግተው በዚህ በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. መጨረሻና በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መዠመሪያ ወር ላይ የግራኝ ጦር በማይደርስበት ተራራማ ሥፍራ ሆነው ከፖርቱጋሎቹ ጋር በመልእክት ብቻ ሲገናኙ ቆይተው እነሆ አሁን ከነርሱ ተገናኝተው የሚቀጥለውን ጦርነት የበላይ ሆነው ለመምራት ተዘጋጅተ ዋል ። በተገናኙም ጊዜ ለፖርቱጋሎቹ የሐር ልብስ መሸለማቸው ለሁለት አንድ ድንኳን አልጋም ብርድ ልብስም እስከማደል መድረሳቸው በዚህ የችግር ጊዜ እን ኳን መጠነኛ ግምጃ ቤትና ንጉሣዊ ድርጅት እንደነበራቸው ያስረዳል ። ጀምስ ብሩስ ያለው እውነት እንደሆነም በዚህ ጊዜ ፫ሺ ወቄት ወርቅ መስጠታቸው በገን ዘብ ረገድም ያላቸው አቅዋም ፈጽሞ ደካማ እንዳልነበረ ያሳያል ።

(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕ. 21 ፤

(2) Histoire du christian. ገጽ 152 - 153

(3) Voyage en Abissinie 2e Vol. ገጽ 203

የቤርሙዴዝንና የካስታንሆዞን ረዘም ያለ አተራረክ በመደገፍ ያገራችንም ታሪክ ነገሥት የወፍላውን ጦርነት ከጠቀሰ በኋላ የንግሥት ሰብለ ወንጌልንና የፈረንጆቹን ካፄ ገላውዴዎስ ጋር መገናኘት እንደዚህ ሲል ባጭሩ አውስቶት ይገኛል። «በጥቅምት ወር አጥናፍ ሰገድ መጥቶ ከእናቱና ከተረፉት ፈረንጆች ጋር በስሜን ምድር ተገናኙ ፤ በዚያም ተማክረው በሸዋዳ ከትመው ተቀመጡ» (1) ። ምንም ቢያጥር እጭሩ ዓረፍተ ነገር ረዘም ያለውን የውጭ አገር ሰዎች አተራረክ በማጽደቁ በታሪክ ፊት መሠረትነቱ ከፍ ያለ ነው ። እንግዲህ በ፲፭፻፵፩ ዓ. ም. በመስከረም ፫ ቀን ፖርቱጋሎቹ ከግራኝ ተዋግተው በተሸነፉ በሚቀጥለው በጥቅምት ወር የተረፉት ፖርቱጋሎችና ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከወፍላ መጥተው በዚሁ በስሜን ተገናኝተው በምክር እዚያው ስሜን ውስጥ ሸዋዳ በሚባለው ተራራማ ሥፍራ ተቀምጠዋል ማለት ነው ።

ካስታንሆዞ ስሜን በገቡ በአሥረኛው ቀን ከንጉሡ ጋር መገናኘታቸውን ሲገልጽ የወፍላው ጦርነት የተደረገው በመስከረም ፫ ቀን ስለሆነ ከንጉሡ የተገናኙት በጥቅምት ወር ከሆነ ከሃያ ቀን በላይ ከወፍላ እስከ ስሜን በጉዞ ላይ ነበሩ ማለት ነው ። እዚህ ላይ አስገራሚው በጦርነቱ ላይ ተሸንፎ በመዝረክረክ ወደ ፊልግ ቀረ? ። ይኸን ቢያደርግ ኖሮ በዘንተራ እቀበት እርሱን ያቀሰለችው ጥይትና ውም ማለት ለግራኝ አሸነፈበት ፲፭፻፵፩ ሆኖ ዝግናውን ክርስቶፎርስን በማሲቀ ለዘለቄታ ሊደመስስ የግዛቱም ዘመን ትንሽ ዘመን ሊቀጥል በቻለ ነበር ። የጠላቶቹን ኃይል

ከዚህ በፊት እንዳልነው ሁሉ ዓፄ ልብነ ድንግል ከወደ መጀመሪያው ላይ ባለ ፈው ድል አድራጊነታቸው ተማምነው ለርሱ የመዘጋጃ ጊዜ ስጥተውት እንዳዋረ ዳቸው አሁን ደግሞ እርሱ ይኸን እላይ ያመለከትነውን የመሰለ ቸልተኛ ቀብረት በማሳየት ለተረፉት ጠላቶቹ ጊዜ ስለሰጣቸው የልብነ ድንግል ልጅ ገላውዴዎስ ትራፊዎቹን ይዘው በርሱ ቸልታ በመጠቀም እርሱን በዘንተራ (ደንቀዝ) እጥር ደው ሊያስገድሉት ይታያል ። በዓለም ላይ የአንዱ ስሕተት ሌላውን እንዲጠቀም ነው ። ያም የተጠቀመውን ያህል ተጠቅሞ በፋንታው በሚያደርገው ስሕተት ሌላ ውን ይጠቅማል ። የዓለም ሕይወት በዚህ ዓይነት ስሕተትና ዘዴ ባለበት ሰንሰለት የተያዘ ነው ።

(1) መሰመርያ ጥቅምት መጽሐ ንጉሥ አጽናፍ ሰገድ (ገላውዴዎስ) መተረክበ ምስለ እሙ መምሕ እለ ተርፉ አፍርንጅ በምድረ ስሜን ። ወተማከሩ ገብሩ ከተማ በሸዋዳ ፣ ታሪክ ነገሥት ገጽ 94 - 95

## ምዕራፍ ፻፳፬

### በግራኝ አህመድ ዘንድ ፪ኛው የጥንቃቄ መጉደል — የአሪያስ ዲያዝ በፖርቱጋሎቹ ላይ መሾም — በወገራ የተደረገው ጦርነት (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ኅዳር ፲፱ ቀን)

በአሁኑ ሰዓት ዓፄ ገላውዴዎስ ከእናታቸው ከንግሥት ሰብለ ወንጌልና ከፖርቱጋሎቹ ጋር ከትመው የተቀመጡበት አገር ሸዋዳ መሆኑን ታሪክ ነገሥቱ አመልክቶናል ። ይኸም አገር በዚያን ጊዜ ከታላቁ ከስሜን ወረዳዎች አንዱ መሆኑን ለማስረዳት ያፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል የዶረና የባርና የሸዋዳ የስሜን አውራጃዎች እያለ ሲጠቅሰው ይነበባል (1) ። በዛሬው የአገዛዝ ድልድል ግን አውራጃው ስሜን ወረዳው ጃናሞራ ምክትል ወረዳው ደረስጌ ሆኖ ሸዋዳ ከደረስጌ (መካነ ብርሃን) ወደ ምዕራብ ከቦላስ ደቡብ ምሥራቅ ከቆሊማ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ በተራራ የተከበበ መንደር ነው ። እንደሰማሁት በዚህ ሥፍራ ሆኖ ትንሽ ጦር ከውጭ የመጣውን ብዙ ጦር በናዳ ብቻ እየተከላከለ ሊመልስ ይችላል ።

ግራኝ አህመድ ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው በአሸንጌ ላይ ባገኘው ድል ተደስቶ ዋናው መሪ ክርስቶፎሮስ ተማርኮ ከሞተ የቀሩትም በሞትና በማይድን ቁስል ቁጥራቸው ስለመነመነ አያሰጉኝም በማለት ባላጋራዎቹን እንደ ምንም አባር ሳያጠፋ ከጦርነቱ ቦታ ጦሩንና ጓዙን እንደያዘ ወደዚያች ለመኖርያ ወደ መረጣት ወደ ለምለሚ አገር ወደ ደምቢያ ሄደ (2) ።

ባንድ ወገን ክርስቶፎሮስን በምርኮ[፬፻፫] ወደ አገራችን እንመለሳለን ሲሉ ከቱርኮች ሳያማክር ራሱን ቆርጦ ስለገደለው በመቀየም የቀሩትም ወደመጡበት ወደ ዘቢድና ወደ ጌታቸው ወደ ፓሻው ለመመለስ ስለወሰኑ የወፍላን ድል ካስዉ በጡት ከእነዚያ ከመጡት ከ፱፻ ምርጥ የቱርክ ተዋጊዎች መካከል ፪፻ በጦርነት ስለሞቱ በሟቾቹ እግር ግራኝ ፪፻ ብቻ ሲያስቀር የቀሩት (፭፻) ወደ አገራቸው ተመለሱ ። ሲመለሱም የዶም ክርስቶፎሮስን ጭንቅላትና ፲፪ቱን ከርሱ ጋር የተማረኩትን የፖርቱጋል ወታደሮች ከነሕይወታቸው ይዘው በመርከብ ተሳፍረው መሄዳቸውን ካስታንሆዞ የአመለከተውን እንብበናል (3) ።

ካስታንሆዞ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ግራኝ አህመድ ከተሸነፍን ቀን አንሥቶ ሁላችንንም እንዳለቅን ቆጥሮት ፫ ቀን ሙሉ ትልቅ በዓል ከአደረገ በኋላ ከብዙ ጊዜ ዝምር ወደተለያቸው ወደ ሚስቶቹና ወደ ልጆቹ ለምለም ወደ ሆነው የዓባይ ምንጭ ወደሚፈልቅበት ከተማው (4) ሄደ ያለው እውነተኛ ነው ።

ባዔ ልብነ ድንግል ላይ ብልህ ተንኰለኛ ዘዴኛ የነበረው ግራኝ አህመድ

(1) ወእምድኅረዝ አጥፍአ ወረኛ ሀገረ ዶረና ወባርና ወሸዋዳ አህጉራተ ስሜን ። Chronica de Susenyos - E. Pereira ምዕራፍ 43 ገጽ 150 ቍ. 28

(2) Histoire du christian. ገጽ 148 - 149 የፖርቱጋሎች ዝማኔነት ገጽ 62

(3) የፖርቱጋሎች ዝማኔነት ምዕ. 19 ገጽ 62 ፤

(4) ያገኑ ደምቢያ ማለቱ ነው ።

አሁን ደግሞ በተራው ሞኝነቱና ቸልታው መታየት ዠምሯል ። ከዚህ በፊት ፖርቱጋሎች ምጥዋ የገቡና ወደ ደባሩዋ የተጓዙ ጊዜ በእጁ የነበረውን ወታደር ግፋት በጥብቅ እየተቆጣጠረ የሚመጣ ርዳታ መከላከል የነበረበትን በቸልታ ፖርቱጋሎቹ ማንም የታወቀ ጦር ሳይቋቋማቸው ወደ ሠራዊ ወደ እንደርታ መምጣታቸውን እንገነዘባለን ።

አሁን ደግሞ ባለፈው እንደጠቀስነው ወልፉ ላይ ባገኘው ድል ተዝናንቶ በመደሰት ከጦርነቱ ላይ የሸሹትን እያባረረ በመግረክ ወይም በመፍጀት ፈንታ እንደ ጦር ሠራዊቱም ብዛት ቀድሞውኑ ከመዠመሪያው ላይ ሊያስከብባቸው ይችል የነበረውን ችላ ብሎ የሸሹት እንደገና ተጠራቅመው እንዲዘጋጁ ከመጣቱ የበለጠ ስሕተቱ ይኸን ፫ ቀን ሙሉ በዓል አድርጎ የተደሰተበትን ድል ያገኘው በቀ ርኮቹ ምርጥ ተዋጊዎች ምክንያት መሆኑን ሲያውቀው የፖርቱጋሎችና የንጉሡ አገራቸው መሰደዱ ነው ። እዚህ ላይ ካስታንሆዞ «እግዚአብሔር ለኛ ቸርነቱን ሁላችንንም እንዳለቅን ቆጥሮን ነበር» ያለው ትክክለኛ ነው ። በእውነትም መሬታና ኩራት ማሸነፍ ያቅተዋል ። ከሰሀርት ድል በኋላ ንጉሡን ሳይዝ ተዋግቶ ያህል ሥቃይና ሞት የተቀበለው ደJSHG ከዚህ ስሕተት እንዳልዳነ አሁንም ግራኝ የወደቀው በዚሁ በወፍላ ያገኘው የጦርነት ድል ባስከተለው ስሕተት ነው ማለት ይቻላል ።

ተርፈው ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር የተገናኙትን የፖርቱጋሎች ቍጥር ካለያን ሆዞ ፩፻፳ ሲያደርገው ያሳነሠው ይመስላል ። በተለይ ደግሞ ከምጥዋ ጦር ያልቀ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ግን በዚህ በወልፉ ጦርነት ሞተው የጉደሉትን የፖርቱጋሎች ቍጥር ፵ ተርፈው ከንዝ ጋር የነበሩትን ፪፻ አድርጎታል (2) ። ያን ከመሰለ መስልምና አሁንም በዚህ አጻጻፍ ከቤርሙዴዝ ካስታንሆዞን ግመን ይቀላል ። ሙሉ ፴ ፖርቱጋሎች ተጨምረዋል ። በዚህ ዓይነት በወልፉው ፪፻ ተርፎች ዋቱ እንዳለው ከነርሱም ወገን ከ፪፻ የበለጠ በጦሩ ሜዳ ላይ ወድቀዋል ማለት ነው (1) ። ጦርነት ምንም ከመከከላቸው ቁስለኛ ቢበዛም ፪፻ ወታደር ተርፎ የሚመለስ እና

እንግዲህ ለነዚህ ላተረፉት ፖርቱጋሎች አሊቀ ከመካከላቸው መሾም የግድ ስለ አስፈለገ ከወፍላ ጦርነት ወደ ሰሜን ገና በጉዞ ላይ ሳሉ አልፎንሶ ካልደይራ ተሾሞ ሲመራ ቆይቷል (3) ። ነገር ግን ይህ ሰው በዚሁ በሰሜን ሳሉ ከፈረስ ወድቆ ስለሞተ በርሱ እግር ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲሾምላቸው ንጉሡ ቢጠይቋቸው

(1) የፖርቱጋል ዠማንነት ምዕ. 20 ፣
(2) Histoire du christ...................... ገጽ 140 - 141
(3) Histoire du christ ................. 141 - 142

ክርስቶፎርስን በመሰለ እግር የሚተካ አለቃ ይቅርብን አለቃችን ሰንደቅ ዓላማዎ ወይም ራስዎ ንጉሡ ይሁኑልን ብለው ማመልከታቸውን ከስታንሆዞ ይገልጻል (1) ።

ነገር ግን በቤርሙዴዝና በኛ ታሪክ ነገሥት በዚህ ጊዜ አርያስ ዲያዝ (2) መሾሙ ስለተጻፈ ምናልባት ውሎ አድሮ ንጉሡ ነገሥቱ ከእናታቸውና ከቤርሙዴዝ ጋር ተማክረው ለፖርቱጋሎቹም የሹም አስፈላጊነቱን አስረድተው ከዚህ በላይ ስሙ የተጠቀሰውን አርያስ ዲያዝ የተባለውን ለዘለቄታ ሾመውታል ማለት ነው ።

አርያስ ዲያዝ የሕንድና የፖርቱጋል ክልስ መሆኑን እርሱም ከሐያ ሁለት ዓመት በፊት እንደ አው. ዘ. ፲፭፻፳ ዓ. ም. ከሮድሪግ ደሊማና ከነአልቫሬጽ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የዶሊጋሲዮኑ ጸሐፊ ለነበረው ለዮሐንስ ስኮላር ( Joao Scolar)እንደ አሽከር ሆኖ መጥቶ ፮ ዓመት ስለተቀመጠ ያገሪቱን ቋንቋ ያውቅ እንደነበረ ከዚህ በፊት ጠቅሰናል ። አሁንም በፖርቱጋሎቹና በኢትዮጵያኑ መካከል ሆኖ በተዋጊነቱ ላይ አስተርጓሚ ሆኖ አገልግሏል ። ምንም ስሙን ለይቶ ባይጠቅሰው ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ደጋግ በደዋርዋ ተገናኝተው ንግግር ሲለዋወጡ በንግሥቲቱ ፊት ተንበርክኮ (3) ያስተረጉም የነበረው እርሱ ሳይሆን አይቀርም ። ቀጥሎ በሰሀርት በግራኝ ላይ የተገኘውን ድል ለንጉሡ ላፄ ገላውዴዎስ ለማብሰር ደጋግ የላከው እርሱን ነው (4) ። ታሪክ ነገሥቱም ዓፄ ገላውዴዎስ ከሸዋ ወደ ትግሬ ሲጓዙ "ፈረንጁ ማርቆስ አብሮ ነበረ — ወነበረ ምስሌሁ ማርቆስ አፍርንጋዊ" ያለውን ባለፈው አንብበናል ።

ISIC

ስለዚህ ይኸንኑ ሰው ንጉሡ ቀደም አድርገው ስለአወቁትና ስለተላመዱት ቋንቋቸውንም ስለሚያውቅ የፖርቱጋሎቹ አለቃ እንዲሆን ከሾሙት ወዲህ ለርሳቸውና ላገሪቱ ታማኝ ሆኖ ወደ አገሩም ሳይመለስ እንዲያውም የካቶሊክ ሃይማኖቱን ወደ ተዋሕዶነት ለውጦ ፤ ለአበሻ እንደበት የማይጥመውን አርያስ ዲያዝ የሚባለውን ነባር ስሙን ትቶ ማርቆስ ተብሎ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ ሲኖር በመጨረሻ ግራኝ ከሞተ ወዲህ የንጉሡ የጦር አለቃ ሆኖ ከጋሎች ጋር ሲዋጋ መሞቱን ወደፊት እናነባለን ።

ዓፄ ገላውዴዎስ በጥቅምት ወር ከእናታቸውና ከፖርቱጋሎቹ ጋር ከተገናኙ ወዲህ በኅዳር ፲፮ ቀን በዚያው በስሜን አቅራቢያ በወገራ የሚገኘውን የግራኝን ጦር አግኝተው ወግተው ሹማምንቱን ሲዲ መሐመድን ፤ ኡስማንንና ጠሊላን መግደላቸውን የቀሩት እንደ ጭስ ተበትነው መጥፋታቸውን ግማሾቹም ደንጊያ እየተሸከሙ መግባታቸውንና በኅዳር ፲፱ ቀን ደረስጌ ወርደው የእስላሞቹን ቤት አቃጥ

(1) የፖርቱጋሎች ዝማንነት ምዕ. 22 ገጽ 66

(2) አንዳንድ ጊዜ አይሬስ ዲያዝ ይባላል ፤

(3) ለአክብሮት ነው ።

(4) የፖርቱጋሎች ዝማንነት ገጽ 27, 89

ለው ንብረታቸውን ማርከው ወደ ሸዋ መመለሳቸውን ታሪክ ነገሥት ያመለክ-
ታል (1) ።

በዚህ በኅዳር ፲፮ ቀን በወገሬ በተደረገው ጦርነት ከግራኝ ወገን ያለውን ጅም
ካስታንሆሶ ሚሬይዝ ግራድ ብሎ የጠቀሰውን ሙሴ ሊትማን ግራድ ዑስማን ያለውን
ገራድ ኡስማንን ማለቱ ይሆናል ብለዋል (2) ። ካስታንሆሶ ጀሙን እንደ ብቻ
ሲያደርገው የኛው ታሪክ ነገሥት ቢጽፍ ከኡስማን ጋር መሐመድ ደግና ጠሊላን
ጨምሯል ። ጠሊላ (ታሊላ) የግራኝ አህመድ የፈረሰኛ ወታደር የነበረ ነው (3) ።

ገራድ ኡስማን (ወይም አትማን) ቢን ጃውሃር ባለፈው የሠራውን ሙሉ በዚህ
በሞተበት ምዕራፍ ላይ መልሰን እናስታውስ ። ከግራኝ ከጦር አለቆቹ አንዱ ሆኖ
በሽምብራ ኩሬና በብዙ ውጊያ ከተካፈለ በኋላ በቀበል ዐፄ ልብነ ድንግልን ሊማ-
ርክ ሲል ለጥቂት አምልጠውታል (4) ። ራስ ወሰን ሰገድ ከሞተ በኋላ ቀውን
ተሾሞ ሕዝቡን ያሰለመ ከአባስ ጋር የሠራዊቱን ተስፋ ለዐልን ቀተሎ የንጉሡን
ያኔ ልብነ ድንግልን የበኩር ልጅ ፊቅጦርን የገደለ እርሱ ነው (5) ።

ስለዚህ በዚህ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. በኅዳር ፲፮ ቀን ዐፄ ገላውዴዎስ እርሱን ከጓደ-
ኞቹ ጋር በመግደል ዓይነተኛውን ያባታቸውን ጠላትና የወንድማቸውን ደመኛ
ገድለው ተበቀለዋል ማለት ነው ። ከዚህ ከሰውዬ ጋር ዐፄ ገላውዴዎስ የተዋጉት
ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ። ባለፈው ያነበብነው ትዝ እንደሚለን ከከፋተኛው ከድልበ
ዓመት በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ከርሱና ከወዚር አባስ እንደያዙሆም ከከፋተኛው ከወዚር ሙጀሂድ ጋር
ኢየሱስ ጋር ከተዋጉ ወዲህ ይኸው ኡስማን ሁለተኛ ጊዜ ከወዚር ያልሆነላቸውን ዓውት ሰበ
ሆና ወግቷቸዋል ። ስለዚህ በፊተኞቹ ጦርነቶች ጊዜ ያልሆነላቸውን
ኛው ጦርነት ጊዜ ቀንቷቸው ገድለውታል ማለት ነው ።

በግራኝ አህመድ ጦር አለቆች ውስጥ ሲዲ መሐመድ ወይም ተገልብጦ መሐ-
መድ ሲዲ (ሰይድ) የሚባሉ ፪ አለቆች መኖራቸውን ዓረብ ፋቂህ የጻፈውን ሙሴ
ረኔ ባሴት ለቅመው የያንዳንዱን አጫጭር ታሪክ ዘርዝረውታል ። ከነዚህ አንዱ የአ-
ብድ ኢን ናስር ጓደኛ የነበረ የፈረስ ዘበኛ (6) ሁለተኛው የዳሞት አገረ ገዥ (7)
፫ኛው ሙሉ ስሙ ከነአባቱ ሲዲ መሐመድ ቢን አሊ ኢልባከሪያ እንድ ጊዜ የግ-
ራኝ ግምጃ ቤት የነበረ አባቱ ዓረብ የዶዋሮ አገረ ገዥ የነበረ ነው (8) ።

(1) ወእምዝ በ፲፮ቱ ለኅዳር (፲፫ የሚል አለ) ገብረ ቀብአ በወገሬ ወቀተሎሙ ለሊሁ ለመሐመድ ወለ
ማን ወለጠሊላ ። እለሰ ተርፉ ተዘርፉ ...
ለኅዳር ወረደ ደረሰኔ ወእውእየ በእሳት አብያቲሆሙ ...
ታሪክ ነገሥት ረኔ ባሴት ያሳተመው ፣ ገጽ 333 ።

(2) የፖርቱጋል ዘመቻ ገጽ 67 ማስታወሻ 53

(3) ዓረብ ፋቂህ በሙሴ ረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 367 ፣

(4) ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 303 ፣

(5) - - - - - - 93 - 94 ማስታወሻ ቍጥር 2

(6) - - - - - - 181 . 313

(7) - - - - - - 399 . 405

(8) - - - - - - 191

ስለዚህ አሁን ከገራድ ኡስማንና ከጠሊላ ጋር ሆኖ ከዓፄ ገላውዴዎስና ከፖርቱጋሎቹ ጋር ሲዋጋ የሞተው የትኛው መሆኑን ለመረዳት ያስቸግራል ። ሙሴ ረኔ ባሴትም የዓረብ ፋቂሀን ዓረብኛውን ወደ ፈረንሳዊኛ ከተረጐሙት ላይ በምልክት የገለጹት አልተብራራም ።

በዚህ ላይ ካስታንሆሦ ክርስቶፎርስ ስሚን ሄዶ አንድ ላንድ ተዋግቶ ከፈረስ ላይ ጣለው ያለው ስሙን ሲዲ አህመድ ያለው በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ውስጥ ሲዲ ሙሐመድ እንጂ ሲዲ አህመድ የሚባል አንድም ስለሌለ ከነዚሁ አንዱን ወይም በዚሁ በስሚንና በወገራ የተሾመውን ከዚህ በፊት ከዶጋሚ ጋር የተዋጋውን በድጋሚ ማውሳቱ ይሁን ወይም የርሱ ምግኤ የሆነው ይሁን በትትክል ለመለየቱ ይቸግራል ።

ሙሴ ሊትማን እንዳመለከቱት በጥንታቄ ካላዩት በቀር በጺሐፊ ዝንጋታ የተነሣ አህመድና ሙሐመድ ብዙ ጊዜ እየተደባለቀ በመጻፍ ይግታል ። ብዙ ጊዜ ባገራችን እንኳን ግራኝ አህመድ በዝንጋታ ግራኝ ሙሐመድ እየተባለ ሲጠራ ኖሯል ።

ምዕራፍ ፻፳፰


የጦር ዝግጅት (፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ጥቅምት-የካቲት)— ከግራኝ ጋር ለመዋጋት የተደረገ ጉዞ — ጦርነቱና የግራኝ አህመድ ሞት (የካቲት ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ.ም.)

ISIC

ዓፄ ገላውዴዎስ ከንግሥት ሰብለ ወንጌልና ከፖርቱጋሎቹ ጋር በጥቅምት ወር በሸዋዳ ከተገናኙ ዠምሮ አሁን ግራኝን ለመውጋት በሚሄዱበት በየካቲት ወር መካከል የአምስት ወር ጊዜ አለ ። በነዚህ አምስት ወራት ውስጥ ግራኝ አህመድ ሊረዱት የመጡትን ቱርኮች አብዛኞቹን ወደ አገራቸው መልሶ ከፋኛ ተመትተ ዋል ብሎ የናታቸውን ጠላቶቹን ፣ ጦር የለውም ምን ሊያደርግ ይችላል ብሎ የሚገ ምተውን ወጣቱን ንጉሥ ገላውዴዎስን በስሜን ትቶ እርሱ በደምቢያ ከሚስቶ ቹና ከልጆቹ ጋር ሆኖ የደስታ ጊዜውን ይቀጥል ዠመር ።

ከሰሀርት ጦርነት በኋላ እስከ ወፍላ ጦርነት ድረስ ያለውን የ፭ ወራት ጊዜ ከስሀርት ጦርነት በኋላ እስከ ወፍላ ጦርነት ድረስ ያለውን የ፭ ወራት ጊዜ ወጣቱ ንጉሥና ፖርቱጋሎቹም እርሱ ተጠቅሞበት እንደነበረ በርሱ አንጻር ያሉት ወጣቱ ንጉሥና ፖርቱጋሎቹም ይኸን የአምስት ወር ጊዜ ለመገናኛና ለመተዋወቂያ ይልቁንም ለወደፊቱ ጦርነት ለመደራጃ ተጠቅመውበታል ። ካስታንሆሦ በእንደዚህ ያለ ጭንቅ ጊዜ ክርስቶፎርስ ለባሩድ ሥራ ቀድሞውኑ አስቦ ይዞት የመጣው ሰው ከጦርነቱ ቦታ ከሞት ተርፎ በእጠገባቸው ስለነበረ ለዚሁ ለባሩዱ ሥራ የሚሆን ጨው ባሩድ ድኝ በነዚሁ በእይሁዶቹ ጋራ ላይ (1) ስለሚገኝ ባሩድ በብዛት እየሠሩ መዘጋጀታቸውን ወደ ምጥዋ ከወፍላው ጦርነት በፊት የተላኩ ፖርቱጋሎች እስኪመለሱ ንጉሡ የጥር ወር በሙሉ በሸዋዳ ማሳለፋቸውን ፤ መላክተኞቹ ግን ሁላችንም ያለቅን መስ

(1) በሎሚን ተራራ በፈላሾቹ አገር ማለቱ ነው




ግራኝ አህመድ ከዜ ገላውዴዎስ ጋር ተዋግቶ የሞተበትን በደንቀዝ የሚገኘውን የወይናደጋ መሬር የሚያሳይ ካርታ

ኗቸው የተረፍነውንም ከንጉሡ ጋር ለመገናኘት የማንችል መስሏቸው በጀልባ እየተሳፈሩ ሄደው ኖሮ በባሕር ነጋሹ ግዛት አለመገኘታቸውን እነርሱን ፍለጋ የሄዱት ሰዎች ወሬውን አመጡልን ሲል ያመለክታል (1) ።

ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ በበኩላቸው ሰው እየላኩ የግራኝን ሠፈር ያሰልሉ ኖር የቀሩት ተመልሰው ከርሱ ጋር ያሉት ፪፻ ቱርኮችና የራሱ ሰዎች ብቻ መሆና ቸውን ከሰሙ በኋላ የግራኝን ጦር ለመከታተል መቁረጣቸውን ጸሐፊው ያወሳል ።

ዓፄ ገላውዴዎስ በጥቅምት ከፖርቱጋሎቹ ጋር ሲገናኙ ተከትኋቸው የነበረ ውን የእግረኛ ጦር ቤርሙዴዝ ሃምሣ ፈረሰኛና ቁጥራቸው ባልታወቀ በባለበቅ ሎኛ ታጅበው መምጣታቸውን የጻፈውን አንብበናል ።

በአሁኑ በአምስት ወራት ድርጅት ግን በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ፰ሺ የእግረኛ ፭፻ የፈረሰኛ ጦር እንደተሰበሰበላቸው ካስታንሆዞ ያመለክትና ይኸን ያህል ሰው ተሰብስቦ ባየን ጊዜ ወደ ንጉሡ ሄደን የዶም ክርስቶፎሮስን ሞት ለመበቀል እንዲ ረዱን ንጉሡን ለመንን ንጉሡም የቁጥራችን ማነስ ምንም እንኳን ቢያሰጋቸው እሺ ብለው ወሰኑ ሲል ካመለከተ በኋላ የልደትንና የጥምቀትን በዓል አክብረው በሠፈር እናታቸውን ንግሥት ሰብለ ወንጌልን አስቀርተው በዚሁ በሁዳዴ ጾም ውስጥ በየካቲት ወር መገባደጃ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በነዚህ ቀስተኛና ሰይፈኛ በሆኑ በ፰ሺ የእግረኛ ወታደር በ፭፻ ፈረሰኞች በ፩፻፳ የፖርቱጋል ወታደሮች በሰ ልፍ ታጅበው ጉዞው ተገምሮ ወገራ ላይ ዶርሶ ሜራይዝ ማእ የሚባል የግራኝ የጦር አለቃ ፫፻ ፈረሰኛና ፪ሺ የእግረኛ ጦር ያለው መኖሩ ስለተሰማ ንጉሡ በሌ ሊት ቀደም ብለው ሄደው ከግንባር ቀደሞቹ ፈረሰኞች ጋር ተጋጥመው አሸንፈው አለቅዬውንም አባርረው ገድለው ጭፍሮቹንም እንደማረኩ ካስታንሆዞ ያረጋግ ጣል (2) ።

ታሪከ ነገሥቱ ከሲዲ መሐመድ ከገራድ ኡስማንና ከጠሊላ ጋር ተዋግተው እሸነፉ ያለው በጥቅምት ወር ነው አሁን ግን ከጉዞ ላይ አግኝተው የተዋጉት በየካ ቲት ወር ላይ ስለሆነ ምንም እንኳን ወረዳው ያው ወገራ ቢሆን በድጋሚ ሌላ ጦር ሊሆን ይችላል ። የሆነ ሆኖ ከተማረኩት ሰዎች ላይ የግራኝን በዚያው በአባይ ዳር መገኘት ወደርሱ ለመድረስም ያምስት ቀን መንገድ እንደሚቀር ከሰሙ በኋላ ጉዟ ቸውን ቀጠሉ ። የጣናን ባሕርና የግራኝን ሠፈር ባዩ ጊዜ እነርሱም በዚያው አቅራ ቢያ ሰፍረው ከዚያ በፊት ከምጥዋ ይጠበቁ የነበሩት ሃምሳ የፖርቱጋል ወታደሮች በመርከብ ተሳፍረው ወደ ሕንድ ሄደዋል የተባለው ውሸት ነው ፤ ወደዚሁ ይመ ጣሉ የሚሉ ወሬ ስለደረሰ ንጉሡ የነዚህ መጨመር ዋጋ ያለው መሆኑን በመረዳት ዝም ብለው ይጠባበቁ ዠመር ።

ይሁን እንጂ ሰሞኑን ከግራኝም ሠፈር ከዚህም ከዔ ገላውዴዎስ በኩል ፈረሰ


(1) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕ. 21
(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕ. 22

ኞች እየወጡ የደፈጣ ጦርነትና ግጭት ያደርጉ እንደነበረ በዚህም ጊዜ አንድ ስመ ጥሩ ዝግና የፈረሰኛ ሹም (አዛዥ) ብዙ ጊዜ በግራኝ ጦር ላይ አደጋ እያደረሰ በጣም አስቸግሮ የነበረውን ግራኝ አህመድ በምን ዓይነት ዘዴ ለማስገደል እስላሰሎ በኋላ አንዱን ፈረሰኛውን ልኮ በንግግር እኔ ብቻዬን ከናንተ ሁለት ፈረሰኛ ይምጣና ለብቻችን እንጋጠም እንዲለውና ያን ጊዜ አዛዡ ፈረሰኛ ብቻውን ወይም ሰው ጨምሮ ሲመጣ አምስት ቱርኮች (1) በሜካ ተደብቀው ርምታ ተኩሰው ይገድሉት ብሎ አዞ ኖሮ ይኸው ስመ ጥሩ አዛዥ በዚሁ ዓይነት ተገድሎ ሰው ሁሉ በርሱ አሟሟት ተስፋ መቁረጡን እያመለከተ ይህ አዛዥ የንጉሡ የአክስት ባል የነበረ መሆኑን ካስታንሆዞ ይገልጻል (2) ።

ስሙ ስላልተጠቀሰ ይህ አዛዥ ማን መሆኑን ለማወቅ ያስቸግራል ። የንጉሡ የአክስት ባል አዛዥ ደገልሃን መልአከ ኃይል (የጦር አለቃ) የሚባለው ነው እንዳ ይባል በደገልሃን ዘንድ እንኳን በአሁኑ ሰዓት ዕድሜው ገፍቶ ሳለ ብዙ ጦር በነበረው በአፍላው ጦርነት ጊዜ ይኸን የመሰለ ዝግንነት እንዳልታየበት ግልጽ ነው ። በአይፈርስ ጦርነት አዝማች ሆኖ ከግራኝ ጋር ሳለመዋጋት ሚስቱን ዓመተ ወጥ ንን (ያፄ ልብነ ድንግልን እህት) ውስጥ ለውስጥ አግላጅ ልኮ በራስ እስላም ስገድ መለወጡን እናስታውሳለን (3) ። ይህ አዛዥ የተባለው ብዙ ጊዜ አዛዥ ሙርጌ ግራ ቢትወደድ ይባል የነበረው ይሆናል (4) ። እርሱም በትክክል አይታወቅም እንጂ ያፄ ልብነ ድንግል አማችነት አለው ከዚህ በፊት ገራድ አህመሽን የግራኝ ገራድ ማታንንና አውራይ ኡስማንን በግሼን አምባ ጦርነት የገደለ እርሱ ነው ። በገዛ እጁ ባይገድልም አሸናፊውና ገዳዩ ጦር በርሱ ይመራ የነበረ ጦር ነው (5) ። ወይም ስሙ በታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ ያልተጠቀሰ የወይዘሮ ሮማን ወርቅ ባል ከሚናስ ጋር የተማረኩት የንላዕከ ማርያም አባት ሊሆን ይችላል ።

የሆነ ሆኖ ቀድሞ በሸዋም በትግሬም የግራኝን ስሙን ሲሰሙ ያርበደብዱ የነበሩት ክርስቲያኖች ሁሉ አሁን ግን የእግዚአብሔር ምሕረት ስለጉበኛቸውና ንጉሡን ገላውዴዎስንና አገልጋዮቹን ስለ እጃናቸው ፊት ለፊት እያዩት ተባለቁ በት ሲል ያሁኑን የካስታንሆዞን አተራረክ በመደገፍ ታሪክ ነገሥቱ በራሱ ቋንቋ ከዚህ በፊት የግራኝን ከዞብል ወደ ደምቢያ መመለስ በወገራ ያፄ ገላውዴዎስን እጅ ናፊነት ከተረከበት አከታትሎ እንደዚህ ይላል «ንጉሡ ከሸዋዳ ተነሥቶ በየካቲት ፳ ቀን ወይና ደጋ ደርሰ ሠፈረ ። ግራኝም ከደረሰጌ ተነሥቶ በንጉሡ አቅራቢያ ሠፈረ ። የንጉሡና የግራኝም ሠራዊት እየተያዩ አብረው ዋሉ ። ወጣት የሆነውን ንጉሡን ገላውዴዎስንና አገልጋዮቹን እንደምን እንዳጸናቸው የእግዚአብሔርን

(1) የቱርኮቹን ቁጥር ቴሌዝ 4 ያደርጋቸዋል ፤ ገጽ 175
(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 22
(3) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 36 ማስታወሻ ቁጥር 3
(4) ገጽ 29 - 33
(5) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 102 ማስታወሻ ቁጥር 3



የማራኝ በር ቀበሌ (ራሴ ያነሣሁት)

ምሕረት ተመልከቱ ። የሸዋም የትግሬ ክርስቲያንም ቀድሞ ስሙን ሲሰሙ ይፈሩ ይንቀጠቀጡ የነበሩት አሁን ፊት ለፊት ተቃርበው የእግዚአብሔር ምሕረት በኑ በኛቸው ጊዜ እየሳቁ ይሳለቁበት ዠመር» (1) ።

ግዕዙ ግራኝን ከደረስጌ ሄዶ ንጉሡ ከሸዋዳ (ስሜን) መጥተው ቅርብ ለቅርብ ሠፈሩ ሲል ካስታንሆዞ ከስሜን በወገራ በኩል አልፈን ጣና ባሕር ዳር የግራኝን ጦር አይተን አጠገብ ሳጠገብ እየተያየን ሰነበትን የሚለው ምንም ያህል ልዩነት የለውም ። ምናልባት ግራኝ አህመድ ከዞብል ወደ ደምቢያ ከመጣ በኋላ ከደምቢያ ወደ ደረስጌ አንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ዓፄ ገላውዴዎስ ከመድረሳቸው ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ደምቢያ ተመልሶ አሁን ለጦርነቱ ከደምቢያ ደረስጌ መጥቶ ከዚያም ንጉሡ ወደአሉበት ወደ ደንቀዝ (ዘንተራ) ሠፈር መጥቶ ይሆናል ።

እንደተለመደው የወታደሩን አሰላለፍ የጦርነቱን አዠማመር ፤ አመራሩንና አፈጻጸሙን በካስታንሆዞ ዓይነት ዝርዝር ሳይሰጥ ታሪከ ነገሥቱ ቀድሞ ስሙን ሲሰሙ ይፈሩ ይንቀጠቀጡ ነበር አሁን ግን እያዩት በመሳቅ ተሳለቁበት ካለው ቀጥሎ እንደዚህ ይላል «የካቲት ፲፯ ቀን ግራኝ በመድፍና በጠበንጃው በቱርኮቹ በመተማመን በትዕቢት እግር ተነሣና ብዙ ዓመታት ሳሳድዳቸው የነበሩት ዛሬ ከፊቴ እንደምን ይቆማሉ አለ ። ንጉሡ አጥናፍ ሰገድ ግን በእግዚአብሔርና በእመ ቤታችን ጸሎት ታምኖ ተቀበለው ። አፊት የቀደሙት የንጉሡ ወታደሮች ከንጉሡ ፊት ሳይቀርብ ገድለውን ግራኝ በር በሚባለው በዘንተራ አቀበት ወደቀ ። በእግዚአብሔር ትእዛዝ በ፫ ሰዓት በዕለተ ረቡዕ ሞተ» (2) ።

በዚህ አነጋገር ግራኝ አጠገቡ ባሉት ቱርኮች በመድፉና በነፍጡ እየተመካ እነዚህ ብዙ ዘመን ሳሳድዳቸው የነበሩት ዛሬ ከፊቴ ለመቆም እንዴት ቻሉ እያለ እየተገረመ በኩራት እግር ሲዋጋ መጣ ሲል ታሪከ ነገሥቱ ያመለከተው ትክክል ሊሆን ይችላል ። በእውነትም ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ እስከዚህ ፖርቱጋሎቹ በሰ ሀርትና በወፍላ እስኪዋጉት ድረስ በተለየ ከሽምብራ ኩሬው ጦርነት (፲፭፻፳፩ ዓ. ም.) በኋላ ግን በፊቱ ቆመ ። አገር ሳገር ንጉሡ ነገሥቱን የማሳደዱ ታሪክ ገና ትኩስ መሆኑ መቼ ይዘነጋል ። ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ቀጥሎ እነአዝማች ተክለ

(1) ተንሥአ ንጉሥ እምሸዋዳ ወበጽሐ ወይና ደጋ እመ ፩ ለየካቲት ወነበረ ሕየ ። ግራኝኒ ተንሢኦ እምደረስጌ ነበረ ሕየ ቅሩበ ኀበ ንጉሥ ። ሠራዊተ ግራኝ ወሠራዊተ ንጉሥ ኅቡረ ወዓሉ ኃበ አሐዱ እንዘ ይትረዓዩ ገጸ በገጽ ። ርእዩ ምሕረቶ ለእግዚአብሔር ዘከመ ገብረ ወዘከመ አጽንዖሙ ለአግብርቲሁ ወለንጉሦሙ አጽናፍ ሰገድ ሕፃን ። ወረሰዮሙ ይትቃረቡ ገጸ በገጽ አኮኑ ነበሩ ቀዳሚ እንዘ ይፈርሁ ወይርእዱ በሰሚዓ ስሙ ለሊሁ ወሸዋ ወክርስቲያን በትግሬ ወይከውኑ ድንጉጻነ ከመ ዘበጽሖሙ ወሰበ ሐወጸቶሙ ምሕረቱ ለእግዚአብሔር ሰሐቅዎ ወተሣለቅዎ . . . . ታሪከ ነገሥት ገጽ 95

(2) ወአመ ፲ወ፯ ለየካቲት ተንሥአ ግራኝ በእግረ ትዕቢት እንዘ ይትአመን በመድፍ ወበነፍጥ ወበቱርክ ወይቤ ዘመጠነዝ ብዙኃ ዓመታት ሰደድክዎሙ ዮምኒ ይቀውሙ ቅድመ ገጽየ ። ንጉሥኒ ተአሚኖ በእግዚአብሔር ወበጸሎታ ለእግዚእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ተመጠዎ ሀራሁሰ ለንጉሥ ዘተቀደምዎ ቀተልዎ እም ቅድመ ይብጽሀ ኀበ ንጉሥ ። ወድቀ በዓቀበ ዘንተራ ዘይሠመይ ግራኝ በር ። ወሞተ በትእዛዘ እግዚአብሔር ጊዜ ፫ ሰዓት በዕለተ ረቡዕ ፤ ታሪከ ነገሥት ገጽ 95 ።

ኢየሱስ እነራስ እስላም ሰገድ እነዓምደ ሚካኤል እነራስ ወሰን ሰገድ የሞቱበትና ደብረ ሊባኖስ የተቃጠለበት ዓመት ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. የዋስሉ አደጋ በቤተ እምሐራ እነዚያ ሁሉ ስመ ጥሩ አብያተ ክርስቲያናት የጋዩበት እነአዝማች አዳሉ የሞቱበት ፲፭፻፳፬ ዓ. ም. እንደርታ ተምቤን አጋሜ አክሱም እየተወረረ ሕዝቡ የተፈጀበት ዓባይ ዶር ሊማረኩ ሲሉ ለጥቂት ያመለጡበት የሠራዬው ተስፋ ልዑል የሞተበት ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. በስሜን በወገራ እነአዝማች ዮሐንስ እነሳውል የሞቱበት ፲፭፻፳፮ ዓ. ም. የውርጅብኝ ዘመናት ነበሩ ። ከ፲፭፻፳፰ ዓ. ም. እስከ ፲፭፻፴ ዓ.ም. ያሉት ዓመታት የጦርነቱና የመከራው ቀንበር ባለፉት ዓይነት ሲታሰብ ,ጋብ ካለ በኋላ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ልጃቸውን ለጋብቻ ጠይቆ እምቢ ካሉት በኋላ በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ወር እንደገና የማባረሩና የውጊያው ነገር ባዲስ የንዴት ኃይል ተቀስቅሶ የፊቅጦርን ሞት የሚናስን መማረክ እንዳስከተለና በዚሁ ታሪክ ነገሥቱ "ንጉሡን ታላቅ ኀዘን ተሜነው" ያለውን ስናስታውስ ያሁኑ የግራኝ አህመድ መገረም ሊያስደንቀን አይችልም ። ቀድሞም እርሱ በድፍረት በሽምብራ ኩሬ ሊወጋቸው ፊት ለፊት የተሰለፈ ጊዜ ልብነ ድንግልን እንደዚሁ ገርሟቸው ነበር ።

የዚህን ሁሉ የድልና የመከራ ጌታ አሁን በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. በየካቲት ወር ወጣቱ ዓፄ ገላውዴዎስ ፖርቱጋሎቹንና የራሳቸውን ወታደር ይዘው በመሸሸና ሲደርስ በመመከት ፈንታ አለበት ድረስ ፈልገው ሄደው ሊወጉት ከፊቱ ሲሰለፉ ግራኝ ነገሩ ገርሞት "እንዴት !" በማለት ብፀፀርለመጠየቅ እንደደረሰ እላይ እንዳልነው በሽምብራ ኩሬ ዋዜማም ግራኝ ባነሰ ጦር ብዙ ሠራዊት ይዘው ከቤተ እምሐራ የሄዱትን ሊገጥማቸው በደፈረ ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል "እንዴት ደፈረኝ እንዳያመልጣችሁ" ብለው ነበር ። ይህ መገረም ያለበት የንቀት ጥያቄ ዓፄ ልብነ ድንግልን ከመሸነፍ ውርደት እንዳላዳናቸው ግራኝም በአሁኑ ጦርነት ከሞት አይድንም ። ጠላትን መናቅ አይገባም የሚባለው ቃል በዋዛ የሚታለፍ አለመሆኑን ይህ ያሁኑ ዘመን የጦርነት ሁናቴ ያሳያል ። ለሚመጣውም ከፍ ያለና የማይዘነጋ በንባብም በቃልም ሊጠና የሚገባው ትምህርት ነው ። በዚያን ጊዜ ጠበንጃና ባሩድ የያዘን ወታደር መናቅ ሞኝነት መሆኑ እንደሚታይ ዛሬም የወታደሩ ቍጥር ቢያንስም በዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀን ጠላት መናቅና በቸልተኝነት መመልከት ራስን አውቆ እንደመግደል ይቆጠራል ።

አሁንም ታሪክ ነገሥቱ ከላይ ያመለከትነውን ከጻፈና የውጊያውንም ወርና ቀን የካቲት ፲፪ ቀን ካደረገ ወዲህ ስለዚህ ስለዓፄ ገላውዴዎስና ስለ ግራኝ እህሲል ይተርካል «በነገሡ በ፫ኛው ዓመት በዕብራውያን የወራት ፍጻሜ ፤ በቅብጣዊ (1) ስድስተኛ ወር በዋነኛው የቤተ ክርስቲያን የጾም ወር (2) በ፲፭፻፴፭

(1) ቅብጣዊ የሚለው የግብጾችን ክርስቲያኖች የኮፕቶቹን አቈጣጠር ነው ። የነርሱም አቈጣጠር እንደኛው ከመስከረም ዠምሮ ስለሆነ የካቲት ስድስተኛ ወር ነው ። የዕብራውያንም እንደኛው መስከረምን የመዠመሪያ ወር ሲያደርጉት ስለማውቅ የካቲትን የወራት ፍጻሜ ያለበት ምክንያት አልገባኝም ።

(2) በየካቲት ወር ላይ የሚውለውን የሁዳዴን ጾም ማለቱ ነው ።



ግራኝ ተመትቶ በቆሰለ ጊዜ ተበሳጭቶ በጕራዴ መታው የተባለው ወይራ ወደቀኝ ያለው

ዓመተ ዓለም (1) በዚህ በተባለው ወር (የካቲት) በ፳፫ ቀን (2) ረቡዕ ጌታችን ማር ገላውዴዎስ ከኢብራሂም ልጅ ከኢማም አህመድ ጋር ተዋጋ ። የርሱም (የአህመድ) የሠራዊቱ ብዛት እንደ አንበጣ ሺ መቶ ሺ ሚልዮን ነው (3) ።


እነዚህም ለውጊያ ሲቆሙ ብርታታቸው እንደ አንበሳ መቅለሳቸው (ፍጥነታቸው) እንደ አንስርት (የንስር አሞሮች) የሆኑ ናቸው ። ከነዚህም ብረት የለበሱ ፈረሰኞች ፤ የቀሩት በጋሻ እየመከቱ በጦርና በጐራዴ የሚዋጉ እግረኞች ፤ ግማሾቹ እንደ ኤፍሬም ልጆች ቀስት በመገተር ፍላጻ የሚወረውሩ (4) እንደ ዩአን ሰዎች በነፍጥ እየተታኰሱ የሚዋጉ (5) አሉባቸው ። ለሚመለከታቸውም ፊቱን ወደ ሰሜን አዙሮ የሚፈላ ድስት መስለው ታዩ ። ሌሎች ደግሞ ደንጊያ በወንጭፍ እየወረወሩ የሚዋጉ በጦርነት ጊዜ ከውጊያ ወደ ኋላ የማያፈገፍጉ ነገር ግን አውሬ እንዳየ የአዳኝ ውሻ ወደ ፊት የመገሥገሥ ልማድ ያላቸው ናቸው ።

የማር ገላውዴዎስ ሠራዊት ግን መጠናቸው (ማነሳቸው) ከወንዝ ላይ የተመረጡትን የጌዴዎንን ሰዎች ያህሉ ነበር ። ነገር ግን ምድያሞችን እንዳለበሰው የገብስ ዳቦ የሚጐርፍ ትልቅ ኃይል ነበራቸው (6) ።

ይሁን እንጂ ማር ገላውዴዎስ ከእስላሞቹ ሠራዊት ከብዛታቸውና ከግርማቸው ከሥራታቸው ከተማመኑው ልባቸው ፊት ሰግጦ አላለም ። የቀድሞ ሁኔታቸውንና የማይሸነፉትን ሰዎች የማይያዙትንም ከተማዎች የያዙትን ሁሉ ሳያስብ ከነርሱ ጋር ለመዋጋት የምንጭ ውኃ እንደጠማው ዋልያ እርሱንም ጦርነት ጠምቶት ነበር ። በርሱና በኢማም መካከልም ትልቅ ጦርነት ሆነ ። ስሙ የተመሰገነ ይሁንና እግዚአብሔር ገላውዴዎስን (ሰላም ለርሱ ይሁንና) በድል አድራጊነት ሸለመው ። ይማም አህመድ ከአሽከሮቹ ባንዱ እጅ ሞተ ። ብዙ ቱርኮችና አዳሎችም ተገደሉ ። ከሞት የተረፉት ግማሾቹ ከይማም ሚስት ጋር ወደ ባሕር (ዓባይ ወንዝ ወይስ ቀይ ባሕር) ሸሹ ፤ ግማሾቹ ተማርከው በገላውዴዎስ እግር ሥር ወድቀው ተገዙለት ። እርሱም መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነ የክፋታቸውን ብድር ሳይመልስ መልካም አደረገላቸው» (7) ።

ታሪከ ነገሥቱ የግራኝን ጦር ብዛት በግዕዝኛ አነጋገሩ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት እያለ ወደ ሚሊዮን የሚያስጠጋው ያነጋገርና ያጻጻፍ ልምድ እንጂ በአሁኑ ሰዓት በአጠገቡ እንኳን ሚሊዮን ሩብ ሚሊዮን የሚደርስ ጦር ያለው አይ

(1) እንዳገራችን ቤተ ክህነት አቈጣጠር ዓለም ከተፈጠረ እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው ዘመን ፭ሺ፭፻ ዓመት ነው ። ጸሐፊው ፭ሺ፭፻ውን ዓመት ክርስቶስ ከተወለደበት ዠምሮ እስከዚህ ጦርነት ድረስ ካለው ከ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ጋር ደምሮ ፯ሺ፴፭ ዓመት አድርጐታል ። ይህም ዓመተ ዓለም ይባላል ።
(2) ወሩና ዓመቱ ዕለቱ ሲስማማ ቀኑ ያኛው ፲፯ ያለውን ይኸኛው ፳፰ አድርጐታል ።
(3) አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት ነው የሚለው ግዕዙ ።
(4) የዳዊት መዝሙር 78 ቍ. 9
(5) እንደ ዩአን ያለው ዮሐንስን የፖርቱጋልን ንጉሥና እንደ ፖርቱጋሎቹ በጠበንጃ የሚዋጉትን ቱርኮች ማለቱ ይሆናል ።
(6) መሳፍንት ምዕ. 7 - 8
(7) ታሪከ ነገሥት ገጽ 101 ። ግዕዝኛው ቃላት ስለሚበዛ እዚህ ላይ ቀርቷል ።



ግራኝ በተይት ተመትቶ የወደቀበት የዘንተራ አቀበት

መስልም ። ካስታንሆዞ ወደፊት እንደምናነበው የግራኝን ጦር ብዙም ሳይጠነቀቅ የተሰለፈ ስለሚያስመስለው ለዚህ ጦርነት በየአውራጃው ያለውን ጦሩን ለመሰብሰብ ከጊዜም ማጠር ከንቀትም የተነሳ ያስከተለውን ጦር በጣም አሳንሶ ያሳያል ። ይሁን እንጂ በማናቸውም ረገድ በርሱ ጦርና ባፄ ገላውዴዎስ መካከል ያለው የሠራዊት መጠን ሲመዛዘን የርሱ በመብዛት የርሳቸው በማነስ በጣም የተራራቀ እንደሚሆን አይጠረጠርም ። የሠራዊቱንም ዝግጅነት በተለይ የቱርኮቹን ውጊያ ወደፊት ከካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ ስናነብ ታሪከ ነገሥቱ ምንም እንኳን ለታሪክ አጋኖና አንዳንድ ቃል እየጨማመረ የተለመደውን ግዕዛዊ አጻጻፉን ለማጣፈጥ ቢፈልግ በመሠረቱ አተራረኩ ከዕውነት አለመዝለሉን እንረዳለን ።

ነገር ግን ጸሐፊው በደፈናው «ሐራሁሰ ለንጉሥ ዘተቀደምዎ ቀተልዎ እምቅድመ ይብጸሀ ኀበ ንጉሥ - ከንጉሡ ፊት ሳይደርስ ቀድመው የሚዋጉት የንጉሡ ወታደሮች ገደሉት» በማለት የግራኝን የገዳይነት ሙያ ለወገኖቹ ኢትዮጵያውያን እንደሰጠው ይታያል ። ነገር ግን በሚቀጥለው ምዕራፍ ገዳዮቹ የፖርቱጋል ተወላጆች መሆናቸውን እንመለከታለን ። ምናልባት ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያውያንና ፖርቱጋሎቹን ባንድ ዘንግ በንጉሣዊ ሥልጣን የሚተዳደሩ የንጉሡ ወታደሮች በማድረግ ጽፎት እንደሆነ አሳቡ ከስሕተት ውጭ ነው ። በበኩሉ ዮሐንስ ቤርሙዴዝና ዢሮም ሎቦ የነርሱንም በመገልበጥ የሚጽፉት እነ ጀምስ ብሩስ ግራኝን አነጣጥሮ የገደለው በተለይ የክርስቶፎሮስ ዳጋማ አሽከር የነበረ ጴጥሮስ የልዮን መሆኑን ያመለክታሉ ። ይኸም አጻጻፍ በኛ ወገን ጸሐፊዎች ዘንድ ጸድቋል ። አንድ ባማርኛ ስለግራኝ አሟሟት የተጻፈ እንደዚህ ሲል ይገኛል «. . . ግራኝ ከመንበሩ ተነሥቶ ሠራዊቱን ሲያሰልፍ ከወዲያ ወዲህ ሲመላለስ በፈረሱ ሆኖ ሁለት ጨሬ ይዞ ፪ አፍ ተራዛሚ ነፍጥ አንግቶ ሠራዊቱ ዝንብ መስሎ ሲታየው ፈረሱ ምን ልርገጥ ሲል ከፖርቱጋል ነፍጠኞች አንዱ ተመልካች ነፍጠኛ ተመልክቶ ኩላሊቱን ቢመታው ከፈረሱ ላይ ወደቀ» (1) ።

## ምዕራፍ ፻፳፯
## የግራኝ አህመድ አሟሟት በካስታንሆዞ አጻጻፍ

ታሪከ ነገሥቱ የማሳጠር ጉድለት ሲታይበት ለዚህ ጦርነት የቤርሙዴዝ አጻጻፍ ደግሞ ቀድሞ ከክርስቶፎሮስ ደጋማ ጋር በሥልጣን አሁን ደግሞ ጳጳስ ልሁን እትጌው መጽሐፍ ላይ የሚነበበው የራሱ መከላከያና የራሱ መከበርያ ነው ። በወልፋ ጦርነት ራሱ ሸሺ የነበረው ባሁኑ በዘንተራ ጦርነት ራሱን በድፍረት ወደፊት ወደ ግንባር እንቅደም ባይ አድርጎ ንጉሡ በሥጋት እንደነበሩ የመሸሽም ፍላጎት እንደነበራቸው ፤ ያ ግራኝ ቱርኮች በጫካ አስደፍጦ ያስገደለው የጦር አሊቃ በሞተና

(1) በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ ያማርኛ ታሪክ ገጽ 39 ።

የግራኝ ጦር እየተጯጯኸ በቀረበ ጊዜ ፈጽሞ ለመሸሽ መወሰናቸውን ራሱ ግን ለፖርቱጋሎቹ የበላይ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ሹም ሆኖ ማዋጋቱን ያመለክ ታል ።

ስለዚህ ለዚህ ከግራኝ ጋር ለተደረገው ጦርነት ከሁሉ የበለጠ እምነት ሊጣል በት የሚችለው የዚህ የሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ጽሑፍ ነው ። እንደ ታሪክ ነገሥቱ ጠቅላላ ሁኔታ ነካክቶ ሳያልፍ ወደ ጦርነቱ ዝርዝር ይገባል ። የፖርቱጋል ወታደር ሆኖ በጦርነት መካከል ገብቶ ውጊያውን በጥቀታ ከመካፈሉ ጋር በሁለቱ መንግ ሥታት ግንኙነት በፖለቲካም ሆነ በሃይማኖት ቤርሙዴዝ ካበቀለው የጠብ ውጭ ስለሆነ አስተያየቱ በትክክለኛ መንገድ ያለፈ ነው ። በራሴ በኩል በርሱ ጽሑፍ የጐደለ መስሎ የሚታየኝ ከዚህ በፊት እንዳመለከትሁት ያበሾቹ ሹማምንት ጦርነ ቱን መካፈላቸው ዝብዱ መሥራታቸው መሞታቸው መቁሰላቸው ሳይቀር ዓረብ ፋቂህ ያደርገው በነበረው ዓይነት የመጠሪያና የማዕርግ ስማቸውን እየጠቀሰ በዛ ሬው ዘመን ካለነው አንባቢዎች ጋር ሊያስተዋውቀንና ያባቶቻችንን መስዋዕትነት ሊያስገነዝበን አለመቻሉ ነው ። ይኸም ለጽሕፈት ሥራ ላልተመደበ ተዋጊ ወታደር ለአገሩ እንግዳ ለሰዉም ለቋንቋውም ባዕድ ለሆነ ሰው ማዳገቱን እያሰብን በዚሁ በፖርቱጋል ቋንቋ ጽፎ በተወልን አመስግነን ወደ ታሪኩ እንለፍ ። እርሱ ያን ጊዜ ባይጽፈው ኖሮ በኋላ ኢኖ ሊትማን ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ሊተረጉመው ከርሱም እነአቶ የና ቦጋለ ወደ አማርኛ ሊመልሱት ባልቻሉ ነበር ።

ISIC

ካስታንሆዞ ወደ ጦርነቱ የተደረገውን ጉዞ ግራኝ አህመድ ከነጦሩ እስከሰፈረ በት ድረስ ያለውን ከተረከው አያይዞ ቀጥሎ የጦርነቱ ለት የሆነውን እንደዚህ ሲል ይቀጥላል ። «ሲነጋ በሰልፍ ሆነን ሳንታ ሚዜሪኮርዲያ (1) ሰንደቅ ዓላማ ፊት ጸሎት አደረግን ። ከዚያም ምሕረቱን እንዲያደርግልን በጠላቶቻችን ላይ ለመበቀ ልና ድል ለማድረግ እንዲረዳን ጌታን ለመንነው ። ቄሱ ጸሎተ ንስሐ ካነበበና ሥር የተ ኃጢአት ካደረገ በኋላ ከሰንደቅ ዓላማው ጋር ግንባር ቀደም በመሆን ከሁለት መቶ ሃምሳ የኢትዮጵያ ፈረሰኞች ከሦስት ሺ አምስት መቶ እግረኞች ጋር ወደ ጠላት ጉዞ ዠመርን ንጉሡ ከሌሎች ሁለት መቶ ሃምሳ ፈረሰኞችና ከቀረው የእግ ረኛ ጦር ጋር ደጀን ሆኑ ። በዚህ ዓይነት በሁለት ተከፍለው የነበሩትን ጠላቶች ገጠ ምናቸው (2) ።

ግራኝ ደግሞ ከሁለት መቶ የቱርክ ተኳሾች ፤ ከስድስት መቶ ፈረሰኞች ፤ ከሰ ባት ሺ እግረኛ ጋር ግንባር ቀደም ሆኖ መጣ ። ግንባር ቀዳሚው ጦር ከሁለት ላይ ተከፍሎ ገጠመን ። አንድ የርሱ የጦር አለቃ ዓንሳ ገራድ (3) የሚባል ከስድስት መቶ ፈረሰኞች ከሰባት ሺ እግረኞች ጋር ደጀን ሆነ ። ደጀን የሆኑትም እንደ ግን

(1) ትክክለኛ ትርጉሙ ግን ቅድስት ምሕረት ሲል ማርያምን ማለቱ ነው ። በኛ ኪዳነ ምሕረት ወይም እመ ምሕረት ከምንለው ጋር ተመሳሳይ ነው ።

(2) ቄሱ ጸሎተ ንስሐ አነበበ የሚለው ቤርሙዴዝን ነው ። የንጉሡንም ደጀን ሆነው አዝማችነታቸ ውን በትክክል ያረጋግጣል ።

(3) ሙሴ ኢኖ ሊትማን ገንጽ ገራድ ያሉት የሚመስል ነው ። የፖርቱጋሎች ዝግንነት ቍ. 55 ገጽ 97

ባር ቀደሞቹ በኃይል ገጠሙን ። ቱርኮቹ እንዳጠቁን ባዩ ጊዜ ፖርቱጋሎቹ በተር
ኮቹ ላይ እየፎከሩ ገብተው ብዙዎቹን በመግደል የቀሩትን ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ
አደረጉዋቸው ። ሰባ የፖርቱጋል ፈረሰኞች ተአምራታዊ ጀብዱ ሲሠሩ ኢትዮ
ጵያውያኑም እነሱን በማየት በበኩላቸው በኃይል ገብተው በመዋጋት መኖራች
ውን አሳወቁ ።

ግራኝ ሰዎቹ እያደር የጦርነቱን ሜዳ እየለቀቁ ወደኋላ ማፈግፈጋቸውን
በተመለከተ ጊዜ ራሱ ከልጆቹ አንዱ ጭምር (1) ይዞ በጣም ወደፊት ቀድሞ
ሲዋጋ ፖርቱጋሎቹ በግራኝነቱ ለይተው አወቁት ። በጣም ቀርበ ባዩትም ጊዜ
በላዩ ላይ አነጣጥረው ሲተኩሱበት አንዱ ጥይት ከደረቱ ላይ አርፎ በእግዚአብ
ሔር ፈቃድ ከኮርቻው እንዲወድቅና ከጦሩ ሜዳ እንዲወጣ አደረጉት ። ሰዎቹ
ከሞት በሚያደርስ ጥይት ቆስሎ መውደቁን ባዩ ጊዜ ተስፋ በመቁረጥ እየሮጡ
ይሸሹ ገመር» (2) ሲል ካስታንሆዞ ባለፈው እንደተመለከተው ኢትዮጵያን ፲፭
ዓመት ሙሉ ያመሳት ግራኝ አህመድ ትልቁ የጦር ዘንዶ ወይም ዝሆን ሊወድቅ
የቻለው በሮምታ ከተተኰሱት ጥይቶች አንዲቷ ደረቱን መትታው እንጂ ቤርሙ
ዴዝ እንደጻፈው የርሱን ጽሑፍ እየተከተሉ በየመጽሐፋቸው እንደ ጻፉት ጴጥሮስ
የልዮኑ ( Pero Leaô ) አነጣጥሮ በመታው በነጠላ ጥይት አይደለም ። ሁለቱ በጦ
ርነቱ ላይ የዋሉት ጸሐፊዎች በዚህ ዓይነት ሲለያዩ ትክክለኛውን ማወቁ ችግር
ነው ። ምናልባት በሮምታ ከተተኰሱት ጥይቶች ውስጥ ጴጥሮስ የተኰሳት በተ
ለይ ጥላው ይሆናል ። ቢሆንም የዚህን ጉዳይ ለብቻው እስከንመለከት ድረስ የጦር
ነቱን ፍጻሜ እንመልከት ።

ካስታንሆዞ የግራኝን ከፉኛ ቆስሎ መውደቅና መሞት የሕዝቡን መሸሽ ካመ
ለከተ በኋላ አንድ የቱርኮች አለቃ በሞቱ ቆርጦ ሽሚዙን ከእጅጌው ወደላይ
ጠቅልሎ ሰፊ ሰይፉን ይዞ በታላቅ ገዦግንነት እየተማታ በዙሪያው በነበረው ተዋጊ
ላይ ፍርሃት መንዛቱን ፤ አምስት የኢትዮጵያውያን ፈረሰኞች ሂደው ለመግደል
ወይም ለመማረክ ሳይሆንላቸው እንደቀረ ፤ አንዱ ኢትዮጵያዊ በጦር ሲወጋው ሲል
ቱርኩ ጦሩን ከእጁ ቀምቶ ጓደኛው የተቀመጠበትን የፈረስ እግሮች እንደመታ
በት በዚያን ጊዜ ጕንዛሎ ፈርናንዴዝ የሚባለው ፈረሰኛ በጦር አስተካክሎ ሲወጋ
ውና ሲጥለው ጦሩ ከፖርቱጋሉ እጅ አልተለየም ኑሮ ስቦ ቱርኩ ከመሞቱ በፊት
የጠላቱን ጉልበት (ቋንዣ ?) በሰይፍ መትቶ ሥሩን በመበጣጠስ ስንኩል አድርጎ
እንዳስቀረውና በመጨረሻ ግን ፖርቱጋሉ ሰይፉን መዞ በመምታት የቱርኩን
ሕይወት እንደጨረሰው ይገልጻል ።

ከዚህ አያይዞ ፖርቱጋሎቹም ኢትዮጵያውያኑም በራሪዎቹን ሲያሳድዱ በተ

(1) ልጁ የተማረከውና በኋላ በሚናስ ለውጥ የተለቀቀው መሐመድ ይሆናል ።
(2) ቤርሙዴዝ «ወደርሱ ሰልፍ መውረዳችን ሲያይ ግራኝ ግራና ቀኝ በሁለት የቱርክ ወታደሮች
ታጅቦ በነጭ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ከፊት ቀደም ብሎ ተዋጊ ወታደሩን ሲያሰልፍ አየነው ። ከዚያ
ከመካከላችን የነበረው ጴጥሮስ የልዮኑ አነጣጥሮ ከፈረሱ ላይ ገለበጠው» ይላል ፤ ገጽ 171 - 172
የነአቶ ዮና ትርጉም አነጣጠሩ ሲል መዝገብ ጣሉበት ይላል ፤ ምዕ. 23

ለይ ፖርቱጋሎቹ ጉዳት ያደረጉባቸውን ቱርኮቹን እያሳደዱ እንደፈጁ ከሁለት መቶ የቱርክ ወታደር ውስጥ ከአርባ በቀር የቀሩት እንደሞቱ ። ያመለጡትም ቱርኮች ወደ ግራኝ ባለቤት ዘንድ መሄዳቸውን ፤ እርሷም የባሏን ሞት ስትሰማ ከጠባቂዎቿ ከሦስት መቶ ፈረሰኞች ጋር ባሏ የተወውን ከፍ ያለ ሀብት ይዛ መሸሿን ፤ በሠፈርም ቀድሞ ግራኝ እየማረከ ያስቀመጣቸውን ብዙ ክርስቲያኖች ግማሹ ሚስቱን ግማሹ እኅቱን ግማሾቹ ሴቶች ልጆቻቸውን ኢትዮጵያውያን በአገኙ ጊዜ የነበረው ደስታ ከፍ ያለ መሆኑን ፤ ብዙዎቹ ክርስቲያኖችም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ወሰን በሌለው ፍቅር ፖርቱጋሎቹን ሁሉ ይስሙ እንደነበረ ፤ ንጉሡም ምርኮውን ሁሉ ከሰበሰቡ በኋላ በዚያ አገር እሀል በብዛት በሚገኝበት በባሕሩ ዳር (1) መቀመጣቸውን ከዚህ በኋላ የተቆረጠውን የግራኝን ራስ እናታቸውና ወዲያው ሕዝቡ ሁሉ እንዲያየው በየአገሩ እንዲዞር ማድረጋቸውን ያረጋግጣል (2) ።

በዚህ ቀን ድልና በግራኝ መሞት ከሁሉ የበለጠ የሚደሰቱት ንግሥት ሰብለ ወንጌል ሳይሆኑ አይቀርም ። ከቤተ መንግሥታቸው ወጥተው በሴት እትም የአገር ላገሩ ዙረት የዘመድ የወገን የልጅ ምርኮና ሞት ያደረሰባቸው የዚህ የሰውዬ እነሚሥ ነው ። ባላቸውን ከሞት ያደረሰ እርሱ ነው ። እምነቱን በወልፋ በተደረገው ጦርነት ሲያድናቸው ባሕር ቆርጦ የመጣው ወጣቱ ክርስቶፎሮስ ዳጋማ ቆስሎ መማረኩን ተማርኮ በሥቃይ መሞቱን የሰሙለት መራራ ለቅሶ ያለቀሱት የሚታወስ ነው ። ሆኖም አሁን ያለፈው ኀዘንና መራራ ለቅሶ ሁሉ በነዚህ በፖርቱጋሎች መሥዋዕትነት በወጣቱ ልጃቸው ድል አድራጊነት ተክሷል ማለት ነው ።

ክርሳቸውም ጋር የራስ ወሰን ሰገድ የአዝማች እዳሉ የነራስ እስላም ሰገድ የነጸሐፊ ላም ሮቤል የነተሰፋ ልዑል የሌላውም የደሀው ሁሉ ቤተ ሰቦች ባሁኑ ሰዓት እንዳሉ በዚህ ቀን ባዩትና በሰሙት ድል ያስራ አምስት ዓመት ኀዘናቸውን ተወ ተውበታል ማለት ነው ። ንግሥቲቱም እነርሱም የግራኝን የተቆረጠ ጭንቅላቱን እያዩ "ይኽ ነው ለካ ! ዕፁብ ድንቅ ነው !" የማለት የመደነቅና የመገረም ስሜት እንደሚያድርባቸው ከዚሁ ካለንበት ጊዜ ላይ ይታየናል ።

በዚህ ቀን ድል በርሱ ጭንቅላት መቆረጥ እነርሱ ሲደሰቱ በፋንታቸው አሁን ኀዘንተኞቹ የባሏን መሞት ስታውቅ የሸሸችው ሚስቱ ባቲ ድል ወንበረና አሥራ አምስት ዓመት በዘረፋ በምርኮ በመግደል ሲደሰቱ የቆዩት ወገኖቹ ናቸው ። ሚናስ የተማረከ ዕለት ፤ ፊቅጦር የሞት ዕለት የሰደተኛዪቱ የኢቴጌ ሰብለ ወንጌል እንዝት አርሮ እንደነበረ በዚያው መጠን አሁን በባሏ በግራኝ ሞት በአጅዋ በሙሐመድ መማረክ የባቲ ድል ወንበራ ልብ በተራው ድንጋጤንና ኀዘንን አዝሎ ይ[illegible]ሻል ማለት ነው ። ይኽ ያዘነ ልብ ወደፊት እንደገና እንሰራርቶ የኑር ቢን ሙጋሂድን ልብ ስቦ በመማረክ የባሏን ገዳይና አንገት ቆራጭ የገላውዴዎስን አንገት ከ፲፪ ዓመት በኋላ ያስቆረጠለት መልሰ የርሷ ልብ ይደሰትና የኢቴጌ ሰብለ ወንጌል ልብ

(1) እንደዚያው እንደ ግራኝ ዓጼ ገላውዴዎስንም በባሕሩ ዳር ተቀመጡ የሚለው በጣና ዳር የሚገኘውን ያንኑ ደምቢያ ይሆን ወይስ በወዲህ በሮገራና በዛሬው ባሕር ዳር ይሆን ፤
(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 23 ።

ISIC

እንደገና ከዘነጋው ኀዘን ጋር መልሶ ይገናኛል ። ኑር ቤን ሙጋሂድ ከድሉ ሜዳ ሲመለስ ጋሎች አዘሎ ላይ ጠብቀው ጦሩን የፈጁበት ጊዜ የተረፈውንም ጦር ራሱ ንና ሕዝቡን በሽታ የጨረሰበት ዘመን ኀዘን ሥፍራውን ከሰብለ ወንጌል ልብ ለቆ ወደ ድል ወንበራ ያዛውራል ። የሁለቱ እመቤቶች ታሪክ ልዩ መጽሐፍ ይወጣ ዋል ።

## ምዕራፍ ፻፳፯

### የግራኝ አህመድ እውነተኛውና አስተኛው ገዳይ - የሞተበት ቀንና ዓመት (፲፭፻፴፩ ዓ. ም. የካቲት ፳፯ ቀን ረቡዕ በ፫ ሰዓት)

ዜና መዋዕል ጸሐፊውና ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ፤ ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ስለግራኝ አህመድ አሟሟት በየበኩላቸው ያቀረቡትን ባለፈው ተመልክተናል ። ሌላ ደግሞ በአሁኑ ምዕራፍ የያዝነውን የግራኝን የገዳዩንና የአገዳደሉን ሁኔታ እንደዚሁ ሲል ጨምሮ በግዕዝ የጻፈውን ትርጓሜውን በአማርኛ እናንብብ «በማርያም ጸሎት ተዋጋው (1) አንድ ፈረንጅ ገድሎት ዦሮውን ቆረጠው . . . . . ከርሱ በኋላ አንዱ ኢትዮጵያዊ አንገቱን ቆርጦ መጥቶ በንጉሡ ፊት እኔ ገደልሁት ብሎ ፎከረ ። ንጉ ሡም ብዙ ሽልማት ሸለሙት ። ነገር ግን ዦሮውን አጥተው ንጉሡ ወዴት ሄደ እያሉ ሲጠያየቁ ያ ፈረንጅ አምጥቶ ስላቀ[illegible] የዚያ የሰውዬ ሽልማት በሙሉ ለፈረ ንጁ እንዲሰጥ ፤ ሰው ሁሉ ይኸን ፈረንጅ በገበያም በአደባባይም በሁሉም ቦታ ብድግ እያለ እንዲያከብረው አዘዙ» (2) ።

ይህ አጻጻፍ የዮሐንስ ቤርሙዴዝን አጻጻፍ የሚደግፍ ነው ። እርሱም ጦርነቱ እንደተዠመረ ፒዬር ደሊዎን (ጴጥሮስ የልዮን) የሚባል ቁመቱ አጭር አነጣጣሪ ተኳሽ ተኩሶ የጌታውን የክርስቶፎሮስን ደም ተበቀለ ያለውን አንብበናል ። ከዚሁ እያይዞ አሯድ የንጉሡ ሹም ግራኝን ከፈረሱ ሲወድቅ ዓይቶ ተንደርድሮ ሄዶ አንገ ቱን ቆረጠውና እኔ ነኝ ገዳዩ ብሎ ለንጉሡ አቀረበ ። ንጉሡም በታላቅ ደስታ አመ ስግና የመንግሥቱ የበላይ አለቃ አድርገ ሾመው ።

ነገር ግን የፖርቱጋሎቹ አለቃ አርያስ ዲያዝ እውነተኛ ገዳዩን ያውቅ የነበ ረው አበሻው እኔ ነኝ ብሎ ጭንቅላቱን ባቀረበበት ሰዓት እዚያው ከንጉሡ አጠገብ ነበርና ግርማዊነትዎ ጭንቅላቱ ስንት ዦሮ እንዳለው እንዲያስመረምር እለምና ለሁ ብሎ ተናግሮ እውነትም ቢፈለግ ካንድ ዦሮ በቀር ሌላው ጠፋ ። . . . . . በዚ ያን ጊዜ ጴጥሮስ የልዮን ተጠርቶ መጣና የተቆረጠውን ዦሮ አቅርቦ ካልተቆረ ጠው ጋር ቢመዛዘን አንድ ሆኖ ተገኘ ። ወዲያው እንዲያውስ በምን መሣሪያ አቁ ስለህ ገደልኸው ብሎ ጴጥሮስ አበሻውን ቢጠይቀው አበሻው ጠበንዣ ያልነበ

(1) ገላውዴዎስ ማለቱ ነው
(2) በሚያልፍበት ቦታ ማለቱ ነው ።



በደንቀዝ ውስጥ ዘንተራ በሚባለው ቀበሌ ግራኝ አህመድ የተቀበረበት ቦታ ባሁኑ ወቅት
(ራሴ ያነሣሁት)

ረው እተኳኩሱንም የማያውቅ ነበርና መልስ ሊያገኝ አልቻለም ። ንጉሡም አፍ ረው አበሻውን ሸሩት ይልና ግዕዙ ያሳየንን የፈረንጁን መሸለም በያለበት እንዲከ በር ያዘዙትን ትእዛዝ ሳይጠቅሰው ያልፋል (1) ። በበኩሉ ጀምስ ብሩስ ከቤርሙ ዴዝ በማመሳሰል እንደዚህ ይላል «በውጊያው ጊዜ ጴጥሮስ ልዮን የሚባል የሚቼ የክርስቶፎሮስ የቀድሞ አሽከር የነበረ ቁመቱ አጭር ቀልጣፋና ፈጣን ሳይታይ ቀስ ብሎ ወንዝ ለወንዝ እየተንሸራተተ አልፎ አነጣጥሮ መታው ። ግራኝ እንደተ መታ ፈረሱን ጴጥሮስ ወዳለበት ሜካ መለስ አድርጎ ለመዋጋት ሲያስብ በትሩ ኃይ ለኛና ከሞት የሚያደርስ ስለነበረ ወዲያው ከፈረሱ ወድቆ ሞተ ። ፖርቱጋሉ ሌላ ውን ጦርነት መቀጠል ስለፈለገ ከግራኝ ጭንቅላት ላይ ጆሮውን ብቻ ቆረጠና ያዘ እንጂ ስለጭንቅላቱ መቁረጥ አላሰበበትም . . . . .» (2) ።


ቤርሙዴዝና ብሩስ አጻጻፋቸው እንደኛው ታሪክ ነገሥት እውነት አድርጎ እንዳጸደቀላቸው ሁሉ ከመሠረቱ እውነት ቢሆንም ንጉሡ አፈሩ ሲል ቤርሙዴዝ ለብቻው የሸልማቱንና የአክብሮቱን ትእዛዛቸውን ያልገለጸው በቂም እርሳቸውን ለተደረገላቸው ዋጋ የማይከፍሉ አስመስሎ በአንባቢ ፊት ዋጋ ለማሳጣት መሆኑ እይጠረጠርም ። በካስታንሆዞ አስተያየት ግራኝ በሮምታ ጥይት የወደቀ መሆኑን ብቻ በማመን ምንም ጆሮውን ቢቆርጥም የጴጥሮስን ገዳይነት በፍጹም ያልተቀበ ለው ይመስላል ። በሁለቱ ወታደሮች መካከል መመቀኛኘት ይኖር ይሆን ? ወይስ በአሮምታ ከተተኰሱ ጥይቶች መካከል "የፈረሱን የመታሁት ጥይት እገሌ የተኰ ሰኝ ነኝ" ብላ እንዲ ጥይት መመስከር ስለማትችል ጆሮን ብቻ ቆርጦ መገኘት ለገዳይነት በቂ ማስረጃ ሊሆን አይችልም ብሎ ይሆን ?

እንደዚሁም ግራኝ አህመድ በዚህ ጦርነት ተመትቶ የወደቀበት ዓመተ ምሕ ረቱ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ወሩ የካቲት ቀኑ ፲፮ ዕለቱ ረቡዕ ሰዓቱ ፫ ተብሎ በታሪክ ነገ ሥቱ ላይ ሲገለጽ የወሩ ቀን ከሌሎቹ አጻጻፍ ጋር ከፉኛ ተማትቷል ። ይህ በመዝ ሙርያ ያነበብነው የካቲት ፲፮ ቀን ረቡዕ ጧት በ፫ ሰዓት ብሏል ። ይህ ቀን ኪዳነ ምሕረት የምትውልበት ቀን ስለሆነ ካስታንሆዞ የሳንታ ሚዜሪኮርድያን (የቅድ ስት ምሕረትን) ሰንደቅ ዓላማ ይዘን ዘመትን ሲል ሁኔታው ይጋጠማል ። ማርያም በዕለተ ቀኗ ትረዳናለች የሚል ተስፋ በእንግዶቹም በነዋሪዎቹም ዘንድ ይኖር ይሆናል ። ደግሞ ፪ኛው ጽሑፍ የካቲት ፳፰ ቀን ማድረጉን አንብበናል ። ሦስተ ኛው ደግሞ ግራኝ አህመድ የሞተው ዓፄ ገላውዴዎስ (ስመ መንግሥታቸው አጽ ናፍ ሰገድ) በነገሡ በ፪ኛው ዓመት ከ፭ ወር ከ፳፪ ቀን አድርጐታል ።

ዓፄ ገላውዴዎስ የነገሡት አባታቸው በሞቱበት ዓመት ወርና ቀን ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. መስከረም ፩ ቀን ሲሆን እስከ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መስከረም ፩ ቀን ያለው ሁለት ዓመት ይሆንና ከመስከረም ፩ እስከ የካቲት ፩ ቀን ያለው ፭ ወር በዚያ ላይ ደግሞ ትርፉ ፳፪ ቀን ሲጨመር ግራኝ የሞተው በየካቲት ፳፯ ቀን ይሆናል ።

(1) Hist. du christianisme ገጽ 174 - 176

(2) Bruce - Voyage ገጽ 205



መቃብሩን ለመጎብኘት በሄድንበት ቀን ከሽማምንት ጋር

ይኸም አንደኛው ጽሑፍ የካቲት ፳፰ ካደረገው ጋር ተቃርቧል ። ሌላ ጽሑፍ ደግሞ «የግራኝ ሞት ንጉሡ አጥናፍ ሰገድ በነገሡ በ፪ ዓመት ለ፯ ወር ፰ ቀን የጐደለው» በማለት በሌላ አነጋገር ቅርጽ ይኸንኑ የላይኛውን አጻጻፍ ያጸድቃል (1) ። እንደ አገራችን አቆጣጠር ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ዘመነ ሉቃስ ማክሰኞ ይብታል ። በዚሁ ዓመት የየካቲት መባቻ ዓርብ ነው ። ስለዚህም በየካቲት ወር ውስጥ የረቡዕ ቀን የሚውሉበት ዕለታት በአራት ሳምንት ውስጥ የካቲት ፯ ፣ የካቲት ፲፫ ፣ የካቲት ፳ ፣ የካቲት ፳፯ ፣ ስለሆኑ ግራኝ የሞተበት ዓመት ወሩና ቀኑ ዕለቱና ሰዓቱ በትክክል የካቲት በገባ በአራተኛው ሳምንት የካቲት ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ረቡዕ በ፫ ሰዓት መሆኑ የሚታመን ነው ።

ቼሩሊ ግራኝ የሞተበትን ከዓረብኛ ጽሑፍ ላይ ተርጉመው በዓረቦች አቆጣጠር በሂጅራ ዓመት ፱፻፵፱ በፈረንጆች አቆጣጠር ፲፭፻፵፫ ዓ. ም. መሆኑን ወሩም የየካቲት ወር ከዜና መዋዕሉ ጋር መግጠሙን ብቻ ገልጠዋል (2) ።

## ምዕራፍ ፻፳፰

## የግራኝ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ችሎትና ጉድለት

የኃይለኛውና የአስፈሪው የግራኝ አህመድ ሕይወት እነሆ በዚህ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. በየካቲት ፳፯ ቀን ረቡዕ ጡዋት በሦስት ሰዓት በደንቀዝ ወረዳ በዘንተራ (በዛንታራ ?) አቀበት በሞት ተፈጸመ ።

ፖርቱጊዞች በ፲፭፻፲፪ - ፲፭፻፲፰ ዓ. ም. መካከል ቁጥራቸው ፲፫ የማይደርስ መላክተኞች ልከው የወጠኑት ወዳጅነት ባገሪቱ ላይ አስቀድሞ የተጸነሰውን የግራኝን ወረራ አጣድፎ የነበረውን ያህል ርዳታው ምንም ቢዘገይ በመጨረሻ ቁጥራቸው ፬፻ የሆነ የወታደሮች ርዳታ በዚህ ጊዜ ደርሶ በዚሁ ርዳታ ወጣቱ ገላውዴዎስ ግራኝን አሸንፈው ክርስቲያናዊ መንግሥታቸውን መልሰው አቆሙ ። ከዚህ በፊት እንዳልነው በግራኝ አህመድ አጥቂነት ያን ያህል መከራ የተቀበሉት አሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ በመከራና በስደት የተሠቃዩት የቤተ መንግሥታቸው ፣ የአብያተ ክርስቲያናቱና የገዳማቱ መቃጠል የወገኖቻቸው እንደበግ መታረድ የጦር አለቆቻቸው እልቂት ንዴቱና ኀዘኑ ያቃጠላቸው ንጉሠ ነገሥት ልብነ ድንግል ይቺን ቀን ሳያዩ መሞታቸው ያሳዝናል ። ነገር ግን ስለርሳቸው መከራውንና ስደቱን አብረው የተካፈሉት ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌልና ልጃቸው ገላውዴዎስ ዓይተዋልና መዋቲው ንጉሠ ነገሥት በሕይወት ባሉት ባለቤታቸውና ልጃቸው ደስታ ነፍሳቸው ተክሳለች ማለት ነው ።

(1) ሞቱሰ ለግራኝ ኮነ እም አመ ነግሠ ንጉሥ አጥናፍ ሰገድ በ፪ ዓመት ወበ፯ አውራኅ ዘእንበለ ፰ ዕለታት .......

(2) L'Islam di ieri e di oggi ገጽ 156 ማስታወሻ ቍጥር 60 ።

ግራኝ አህመድ ይኸን ሁሉ ግፍ በጭካኔ ፲፭ ዓመት በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ያስቻለው በርሱም ውስጥ የሱማሌና የአዳል ተወላጆች ለግፉ ሥራ ተባባሪ የሆኑበት የታሪክ ምክንያት እንዳለ በበኩላችን መገንዘብ አለብን ። እንደ ግራኝ ያህል አይብዛ እንጂ ከዚህ በፊት እንደጠቀስነው ከይኩኖ አምላክ ዝምርር እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ከሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት በበለጠ ጊዜ ውስጥ የወላስማ ባላባቶች የዘይላ ሹሞች በሸፈቱና ግብር በከለከሉ ቍጥር አንዳንድ ጊዜም እንደ አሁኑ እንደ ግራኝ ክርስቲያናዊውን መንግሥት ገልብጠን የእስላም መንግሥት እናቆማለን በሚሉ ምኞት እየተነሡ በተሸነፉ ቍጥር በክርስቲያኖቹ እጅ መስጊዳቸው እየፈረሰ በመሪዎቹና በቤተ ሰቦቻቸው በነዋሪውም ሕዝብ ላይ አልፎ አልፎ የዘረፋ የቃጠሎ የመግደል ግፍ በክርስቲያኖቹ እጅ አልተፈጸመባቸውም ማለት አይቻልም ።

ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ መሐመድ በድላይ ሸፍቶ ተዋግቶ የሞተ ጊዜ ዓፄ ልብነ ድንግል ማኀፉዝን ያሸነፉለት አካላቸውን ከየመለያልዩ በማስቆረጥ በነርሱ ላይ ያደረጉትን ማንበብ ይበቃል (1) ። ነገሥታቱ ከይኩኖ አምላክ ዝምረው እስከ ልብነ ድንግል ድረስ በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ አልፎ አልፎ ያደረጉትን መጠነኛ ግፍ ግራኝ አህመድ ወልደ ኢብራሂም ባጭር ጊዜ በ፲፭ ዓመት ውስጥ በእጥፍ ተበቅሏል ማለት ነው ።

አሁን ግን እርሱ ሲ፲፱፻ እርሱና ደጋፊው የቱርክ መንግሥት ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን መንግሥት ገልብጠው እንደ ግብፅ እንደ ዓረብያ ኢትዮጵያን እስላማዊ መንግሥት ለማድረግ ተወጥኖ ከጫፍ ደርሶ የነበረው አሳብ ተመልሶ ፈረሰ ። ዓረቦችም ቱርኮችም እንደገና የቆመውን ክርስቲያናዊ መንግሥት ለመገልበጥ የሚያስችል ወታደር ወደ ኢትዮጵያ አልላኩም ። ግራኝ አህመድ ሲሞት እርሱን የመሰለ ዝግናና ደፋር መሪ ከአዳልና ከሱማሌ ወይም ከወላስሞቹ ባላባቶች ውስጥ እንደገና አልተነሣም ።

የእኅቱ ልጅ ኑር መሐመድ (የወዚር ሙጃሂድ ልጅ) ቢነሣም የአነሣሱ ዋና ዓላማ ድል ወንበራን ለማግባት እንጂ ኢትዮጵያን በግራኝ አህመድ አቅድ ለመግዛት ስለ አልነበረ ላግባሽ ብሎ የለመናት ድል ወንበራ የባሏን ገዳይ ግደልና አግባኝ ካለችው በኋላ በጦርነት ቀንቶት ዓፄ ገላውዴዎስን ገድሎ በዚሁ ምክንያት የግራኝን ሚስት እንዳገባ በዚያው ዘመን ባፄ ገላውዴዎስ መንግሥት ላይ የተነሡት ጋሎች በርሱም ላይ ተነሥተው ካጠቁት በኋላ በዚያው ባገሩ ቆመ እንጂ ወደ ፊት ገፍቶ የኢትዮጵያን መንግሥት ሊያነቃንቅ አልቻለም ። የጦርነቱንና የፍጻሜውን ሁኔታ ወደፊት እንመለከታለን ። ግራኝ አህመድ የጦርነቱ ታሪክ በዚሁ በኢትዮጵያ ውስጥ ተሸፍኖ ይቅር እንጂ በጦር አመራሩ በአወጋጉ ዘዴና ስልቱ በድፍረቱና በጭካኔው በምኞቱ ብዛት በአሳቡ ስፋት በዓለም እንደተነሡት ታላላቅ ወራሪዎች ለመምሰል ምንም ያህል አይቀረውም ። አረስቶትን የመሰለ

(1) የኢ.ት. ታሪክ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕራፍ 35 ገጽ 180 - 194

መምህር አግኝቶ በከፍተኛ ጽርዓዊ ትምህርት ታንጾ ቢሆን እንደ እስክንድር ፤ በብ ሪዩን የፈረንሳዊኛ የወታደራዊ አካዳሚ ትምህርት አድጎ ቢሆን እንደ ናፖሌዎን ለመሆን ምንም እንደማያጉድለው ባለፉት በጦርነት ምዕራፎች ያሳየው ዘዴና ድፍረቱ በሰፊው አመልክተውናል ። በመጨረሻ ጊዜ ባለፈው ግራኝ ያሳያቸው የዝንጋታ ስሕተቶች እንግሊዝን ሳይጥል ወደ መስኮብ ዘምቶ ተዋርዶ ከተመለ ሰው ከናፖሌዎን ስሕተት ጋር ይመሳሰላል ። ሂትለርም ሙሶሊኒም ይኸን በመሳሰ ለው ስሕተት አልፈዋልና የርሱ ሊያስገርም አይችልም ።

ከተራ ሰውነት እንዳዬ ቴዎድሮስ ተነሥቶ ከወላስማ ዘር የወረደውን የሐረ ሩን ሡልጣን አቡበከርን ከመገልበጥ ልጁን መሐመድን የጭፍራ ያህል ለማድረግ ደርሶ ከዚያ እርስ በርሱ የማይዋሐደውን ልዩ ልዩ የአዳልና የኢሳ የሱማሌ ነገድ በፍቅርም በኃይልም ባንድነት አስተባብሮ ለማንም የውጭ መንግሥት ያልተበገረ ውን ታላላቆቹ ባላባቶች እነሐቀዲን እነሰበርዲን እነመሐመድ በድላይ እነኤሚር ማኅፉዝ ሞክረው የጠፉበትን ዓላማ በማከናወን የደረጀውን የኢትዮጵያን መንግ ሥት ገልብጦ በአስቸጋሪው የክርስቲያን መንግሥትና ሕዝብ ላይ የራሱን እስላ ማዊ ሥልጣን እመዘርጋት ደረሰ ። ጦርነቱን ከገረመረ እንሥቶ እሁን በወፍላ የፈ ለመችው የፖርቱጋሎቹ ጥይት በዚህ በዘንተራ ዓቀበት ደረቱን ሰብሮ ሕይወቱን እስክታሳጣው ድረስ የጦር ስልት ከማወቁ የተነሣ አውቆ ማያት ላይ እንዳደረገው ካልተወ በቀር ፖርቱጋሎቹ ከመምጣታቸው በፊት ጦርነት ገጥሞ ያላሸነፈበት ቦታ የለም ። ነገር ግን ከኩራቱና ከዕብሪቱ የተነሣ ራስ ወሰን ሰገድ ለጻፈለት መልስ ሲሰጥ «የሚዋጋን ጦር አጣን» ያለውን ስናስታውስ ዞሮ ዞሮ ያ ሁሉ ኩራት እነሆ ከውድቀት አላደነም ። በነራስ ወሰን ሰገድ በነአዝማች አዳሉ ሊፎከርባቸው የቻለው በንጉሡም ላይ ልጅህን ስጠኝ አለዚያ ከእጄ የምታመልጥበት ሥፍራ የለ ህም ብሎ የዘበተባቸው ከነርሱ ጋር ባሩድና ጥይት ስለሌለ ብቻ ነው ። እንደ ልብ አናጋሪ የሕይወትና የሞት መፍትሔውም መሣሪያ መሆኑን ከዚህ በፊት ካየነው የበለጠ ባሁኑ የግራኝ ውድቀት የበለጠ እንመለከታለን ። ጀምስ ብሩስ እንዳለው ጴጥሮስ ልዮን ሸለቆውን ተንሸራቶ ወርዶ አድብቶ በዚያች ጥይት ከፈረሱ ባይገ ለብጠው ኖሮ የክርስቲያናዊው መንግሥት ዕድል ሌላ ምን ኖሯል ።?

ከሥር ዠምሮ እስከ ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ድረስ ብዙ ጊዜ እየገበረ ሲገዛ አንዳንድ ጊዜ ሲሸፍት ሲመታ ሲማረክ ከኖረው ከአዳልና ከሱማሌ ውስጥ ከመለሳይ ወገን አንድ ሰው ተነሥቶ ይኸን የመሰለ ያልታሰበ የጦር አደጋ አንሥቶ ነዋሪውን መን ግሥት ከመገልበጥ ይደርሳል ብሎ የጠረጠረ ባለመኖሩ ከደዋሮ ዠምሮ እስከ ሐማ ሴን ከድል ወደ ድል እየተራመደ ንጉሡን ከነጦራቸው ሲያሳድድ በፊቱም የሚ ቆም ጦር እየጠፋ ሁል ጊዜ አጥቂ ሁል ጊዜ አሸናፊ መሆኑን የተመለከተው የዚ ያን ዘመን ሕዝብ ለዚህ ክንውን የረዳው ከሰውነት የተለየ ሰውነት ከችሎት በላይ የሆነ ችሎት ቢኖረው ነው ብሎ የፈጠረው ተረታዊ የግራኝ ታሪክ እስከ ጊዜያችን የደረሰውን የማያውቅ የለም ።

በዚህ ተረታዊ ታሪክ ግራኝ ከሰው በላይ የሆነ ልዩ ፍጡር ሰውነቱ ጉልያ

ዳዊ የሚዋጋበት ጦር ቁመቱ እስከ አርባ ክንድ የሚደርስ ጥይት በላዩ ላይ እንደበ
ረዶ ሲዘንምበት የትንኝ ያህል የማይቀነቅነው ወይም የሚቀነቅነው ቋጥኝ የሚያህ
ለውን ደንጊያ ሊወረውር የሚችል እስከ መባል ደረሰ ። ይኸንንም ሕዝቡ ፈጥሮ
ከማውራት የደረሰው የግራኝን ከማንም ያልተለየውን ሰውነቱን ለይቶ ራሱ በተፈ
ጥሮ ያለውን የአመራሩን ዘዴ በዘመኑ ከውጭ የሚያገኘውን የሰውና የመሣሪያ
ርዳታ ገልጾ በጽሑፍ ያቀረበለት ስለሌለ ፤ በታሪክ ነገሥት ውስጥ ያለውም አጫ
ጭሩ ነገር ግን እውነተኛው በግዕዝ የተጻፈው በየቤተ መንግሥቱ ወይም በየገዳ
ማቱ ተደብቆ ስለኖረ በምንም ዓይነት ይሁን እንደዚህ ለጐላው የወረራ ታሪክ ካህ
ንም ሕዝብም አንድ አሳቡን የሚያሳርፍበት ታሪክ ራሱ መፍጠር ግዴታ የሆነበ
ትን ባለፈው በግራኝ አነሣሥ ላይ አንብበነዋል ። ይኸን እስከ ቅርብ ጊዜ ታሪክ
ሆኖ የኖረውን ዛሬ ተረታዊ ታሪክ ብለን መድበነዋል ።

ከተዋጊነት ይልቅ መንፈሳዊነት የሚያጠቃቸው ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል
ራሳቸውም ለዚሁ ከመንፈሳዊነት ተዋጊነት ለሚታይበት ጽኑ ባላጋራቸው የሰ
ጡት አስተያየት ከሰውነት ወደ ሰይጣንነት የዞረ ነው ። በሚያስገርም ፍጥነት እየ
ተከታተለ ዋስል ደርሶ የርሳቸው ወገኖች ሳያውቁ አድብቶ ከሠፈራቸው ከሐን
ደርሶ በግራ እጁ እየተማታ ሲዋጋ እርሳቸው ባንድ ጫካ ውስጥ ተደብቀው እያዩት
«በሰው የተመሰለው ሰይጣን ያውላችሁ» የአሉትን አንብበናል ።

ነገር ግን በገራድ አበ፲፮፲፪ት በሆባት ቀበሌ (ድሬዳዋና ሐረር መካከል ?) ያደ
ገው የኢብራሂም ልጅ አህመድ እንደማናቸውም የሰውነት ፍጡር ያለው ሰው
ሲሆን ሰውነቱን እንደብዙ መሪዎች ተንኰለኛነት ዘዴኛነት ሲያስፈልግ ደፋርነት
ተዋሕደውታል ። እንደናፖሌዎን አዘንግቶ በማድባት በአወጋግ ዘዴ በትንሽ ጦር
ብዙውን መበታተን ሲችል እንዳነበብነው በዚያው መጠን አገርና ከተማ በያዘ
ጊዜ እንደ አቲላ አገር አማሽነት ይታይበታል ። እንደሮማውያን አለያይቶ የመግዛ
ትንም በምርኰኛ የመጠቀምንም ዘዴ ሁሉ ያውቅበታል ።

ስለዚህ ይህ ሁሉ ሐተታ ተደምሮ ግራኝ አህመድ ምን ዓይነት ተዋጊና የጦር
መሪ እንደነበረ ያስገነዝበናል ። ባላጋራነቱ አጥቂነቱ በ፲፭ ዓመት ውስጥ በክርስቲ
ያናዊው ሕዝብ ላይ የሠራው ከባድ ግፍ ሳይዘነጋ በጦር አመራሩ በዘዴው በድፍ
ረቱ በተለይ በወገኖቹ ዘንድ ምሥጉን ሆኖ ቢከበር ቢመሰገን በክርስቲያኖቹም
ዘንድ ስሙና ሥራው ቢተረት ቢደነቅ የተገባ ነው ። በዚህ ምክንያት ይኸን መሪ
እስላሞቹ "ሳሂብ አል ፋትህ - ድል አድራጊው" እንደሚሉት (1) የኛም ጸሐፊ
ዎች እነአዛዥ ዘወልደ ሃይማኖት "ግራኝ የመለሳየች የበላይ ፤ ሥልጣኑ ከዘይላ
ባሕር እስከ ደሆኖ ወደብ የደረሰው ፤ ያሸናፊዎች አሸናፊ ፤ የኃያላኖች ዙፋን አፍ
ራሽ" በማለት ያወደሱትን ከዚህ በፊት አንብበናል ።

ነገር ግን ባለፈው እንደተመለከትነው ግራኝ አህመድ የኢትዮጵያ ወረራ
ቀንቶት ሚስትና ዕቁባት አብዝቶ በጌትነት በተድላ በደስታ በደምቢያ ተደላድሎ

(1) La letteratura etiopica-E. Cerulli ገጽ 117

ተዘባኖ ከመቀመጡ በፊት የነበረው ትጋቱ ዘዴው ጠርጣሪነቱ በጊዜ ብዛት ደብዝዞ በፊት ከነበረው ከጦርጦራነቱ ከተንኮሉ ጋር በኋላ ያሳየውን ቸልተኝነት ስና መዛዝነው ያንድ መሪ ጠላቱ ማሸነፉ ከማሸነፉ በኋላ የሚቀጥለው ሥራ ፡ ከዚያ ተከታትሎ የሚመጣለት ተድላና ደስታ ነው ። በድምር እንደ ሮማ ያሉት ታላላቅ የቄሣር ግዛቶች ሁሉ የሚወድቁት በዝርዝር የሚገኙት ወራሪዎችና ጨቋኞች የሚገለበጡት ይኸን በመሳሰለው መንገድ ነው ።

አሁንም ያን የመሰለ ዝግና ጠርጣሪ አገሪቱን ከዳር እስከ ዳር ወርሮ በደም ቢያ ተደላድሎ የድሉን ደስታ ልቡን ሊያዘንጉት ከቻሉት ከዕቁባቶቹና ከሚስቶቹ ጋር በሚያጣጥምበት ሰዓት ዓይነተኛ ተግባሩን እንደረሳ አይጠረጠርም ። ዓይነተኛ ተግባሩ ሆኖ የሚሰማን ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የምጥዋን ወደብ በብርቱ ጦር እያስጠበቀ ቢያስፈልግም በዚያ ላይ ጠንክሮ አለመዋጋቱ ነው ። መቼም ከወረራው በፊት በኢትዮጵያና በፖርቱጋል መንግሥታት መካከል የተወጠነውን ወዳጅነት በዝርዝር በተለይ አገሪቱን ከያዘ በኋላ እንደሚሰማው ጥርጥር የለውም ። የፖርቱጋሎም የመርከብ ኃይል በየወደቡ ከቱርክ መርከቦች ጋር መጋጨቱን ወደ ርሱ ከሚመላለሱት ቱርኮችና ዓረቦች እንደሚረዳው እርግጥ ነው ።

ይኸ ሲሆን ከሊስቦንም ይሁን ከጐአ የፖርቱጋል መንግሥት ርዳታ ሊመጣ የሚችለው በምጥዋና በዘይላ ወደብ መሆኑን ጠርጥሮ በጥብቅ ያላስጠበቀው ያው የቀድሞው አሸናፊነት የፈጠረበት ሥራት ከብልጽግና ከደስታ ጋር ዝንጋዔን በላዩ ላይ ፈጥሮበት መሆኑ አይጠረጠርም ። ሁለተኛ ደግሞ በወፍላ ለመገርመሪያ ጊዜ የመሸነፍ የመቁሰል ውርደት በደረሰበትና ለዚህ ውርደት ማደሻ የሚሆነውን የቱርክ ወታደር በብዛት በምሥጢር አስመጥቶ ሳለ ባስመጣው ወታደር ምክንያት ማሸነፉን ሲያውቀው ፭ኛ. የተሸነፈውንና የሸሸውን ጦር ባዲስ የአሸናፊነት ጉልበት ተከታትሎ አለማጥፋቱ ፤ የሸሹት ከንጉሡ ተገናኝተው በሞራልም በመሣሪያም ደርጅተው እንዲወጉት የ፫ ወር ረዥም ጊዜ መስጠቱ ። እነዚህን ጠላቶቹን በዚህ ዓይነት አስቀምጦ በወፍላ ድልን በእጁ አቅርበው የሰጡትን የቱርክ ወታደሮች አስቀይሞ ወደ አገራቸው መመለሱ ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል በሰላሙ ቀን ሳይደራጁ ከሩቅ አገር ለዝምድና የመጡትን ፖርቱጊዞች ደጅ የማስጠናትና የቸልታቸውን ዋጋ በስደትና በመከራ እንደከፈሉ ግራኝም እላይ ባመለከትናቸው ምክንያቶች እርሳቸው በወደቁበት የስሕተትና የዝንጋታ ጉድጓድ ወድቆ ዋጋውን በመሸነፍና በመሞት አንገቱንም በመቆረጥ ከፍሏል ። አንዱ ካልዘነጋ የሌላው ትጋት አይታይም ፤ አንዱም ካልተሳሳተ ሌላው አይጠቀምም ። የተጠቀመውም ባንድ ጉድለት የተነሣ መልሶ ካልተሳሳተ ሌላው የመጠቀም ፋንታ አያገኝም ። እንደዚህ ያለውን የተፈጥሮ ሕግ ለመሻር ሀብትም ብልጠትም የሠራዊት ብዛትም ያለፈ ዝናም መፈራትም አያስችሉም ። እነዚህ ሁሉ ግራኝ አህመድ ነበሩት ። ሁሉም ተሰብስቦ ያለበት ይህ አካል ባንዲት ጥይት ፈርሶ ተሻረ ። ግራኝ በማሰኘት ስመ ጥር አድርጋው የነበረችው ግራ እጁ እንደማንም እጅ አብራ ወደቀች ። የብዙ ሰው ሕይወት ወዳፈር እንደላከች እርሷም ወዳፈርነቷ ተመለሰች ።

የግዛቱን ዘመን ዓፄ ልብነ ድንግልን በሽምብራ ኩሬ ካሸነፈበት ከ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. መጋቢት ፲፩ ቀን ዠምሮ እስከ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. የካቲት ፳፪ ቀን ያለው ሲታሰብ ፲፬ ዓመት ከ፲ ወር ከ፳፮ ቀን ይሆናል ። በእስላሞቹ አስተሳሰብ ግራኝ ኢትዮጵያን ድል አድርጎ የያዘው በሂጅራ ዓመት ፱፻፴፯ ዓመት በኛ ፲፭፻፳፱ ዓ. ም.) ይሆንና የሞተው በሂጅራ ዓመት ፱፻፵፱ (፲፭፻፴፭ ዓ. ም.) ሆኖ የገዛበትን ዘመን ፲፪ ዓመት ከ፮ ወር አድርገውታል (1) ።

## ምዕራፍ ፻፳፱

### ከግራኝ አህመድ ሞት በኋላ ስለተረፈው ጦርና ስለድል ወንበራ ሽሽት– በግራኝና በኢጣልያ ወረራ ዘመን ያገልጋዮችና የከዳተኞች ተመሳሳይ ዕድል ።

ታሪከ ነገሥት አዘጋጂው ገና ግራኝ ከመሞቱ ቀደም ብሎ ዓፄ ገላውዴዎስ በወጣት እግርና ዕድሜያቸው ከትግሬ ወደ ስሜን ከስሜን ወደ ሸዋ እየተዘዋወሩ በደፈጣ ጦርነት ቊጥሩ ባነሠ ጦር የተበታተነውን የግራኝን ጦር እየወጉ የተሰፋ ጮራ ማሳየታቸውን ለማመልከት ባንድ ቦታ «ማር ገላውዴዎስ በነገሡ በ፪ኛው ዓመት ቤተ ክርስቲያን የማሸነፍን ጸጋ ለበሰች » ይላል ። ያገሪቱን ጠቅላላ የማሸነፍና የትንሣኤ ጒዳይ ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ ጸሐፊው የቤተ ክህነት ሰው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሕዝበ ክርስቲያኑን ደኅንነት ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ ጒዳዩ የተያያዘ ነው ።

በሌላ ቦታ ደግሞ ታሪኩን አዘጋጅው ሁልጊዜ የቤተ ክህነት ሰው እንደመሆኑ መጠን ዓረብና ቱርክ አዳልና ሱማሌ ባንድ ወገን አበሾቹና ፖርቱጋሎቹ በሌላው ወገን ሆነው የተላለቁበትን ጦርነትና በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ መሪነት በፖርቱጋሎቹ ጥይትና ባሩድ ኃይለኛው ግራኝ የወደቀውንና የተገኘውን አሸናፊነት አሁንም ወደ ቤተ ክርስቲያን በማስታከክ «ሞዓት ቤተ ክርስቲያን ላዕለ ነገደ ተንባላት - ቤተ ክርስቲያን በእስላሞች ላይ አሸናፊነት አገኘች» ብሏል ። ፊደሉን ተከትለን ነው እንጂ እንደእውነቱ አሳቡ በእስላሙ በግራኝ ወረራ ልትወድቅ ወይም ወድቃ የነበረችው የክርስቲያን አገር አሁን ከግራኝ ሞት በኋላ ትንሣኤ አገኘች ለማለት ነው ። ወይም እላይ እንዳልነው ክርስቲያኖቹ በእስላሞቹ ላይ አሸናፊነትን አገኙ ለማለት ነው ። በፊት ላፄ ልብነ ድንግል መንግሥት ውድቀት ምክንያት የሆነው ከውጭ የመጣው የወታደርና የመሣሪያ ርዳታ እንደነበረ አሁንም ለግራኝ አወዳደቅ ምክንያት የሆኑት ለጥይት የሚሆን ባሩድ መሥራት የቻሉት ጠበንጃ በእጃቸው የጨበጡት ፖርቱጋሎች ናቸው ። ይሁን እንጂ የወጣቱ ንጉሥ አመራርና ለርሳቸው ሲል የተሰበሰበው የእግረኛና የፈረሰኛው ጦር ከነሹማምንቱ በበኩሉ የቤተ ክህነቱም ክፍል ተካፋይነቱ ስለማይቀር መከራው ኀዘኑ የጋራ እንደነ

(1) L'Islam d'ieri e di oggi - E - Cerulli ገጽ 156 ቊ. 60 ።

በረ ድሉም ደስታውም የጋራ ነው ቢባል የተገባ ነው ።

ኃይለኛው ግራኝ ሳበሾቹ ክርስቲያኖች ለብቻቸው እንዳልተበገረ ጠበንጃ ለያዙት ወታደሮችና የክርስቲያን በቀል ለጠማቸው ለፖርቱጋሎቹም አልተሸነፈም ። ለዚህ የወፍላው ጦርነት የክርስቶፎሮስ ደጋማ ሞት ምስክር ነው ። የእሁኑም ጦርነት በበላይ በንጉሡ ነገሥቱ ባይመራ የአበሾቹ ኅብረት ባይጨመር ኖሮ እነዚያ የተረፉ ፩፻፸ ፖርቱጋሎች ሊያሸንፉት እንደማይችሉ እርግጥ ነው ። ያለ ዚያ በሸዋዳ ሠፍረው ሳሉ እባክዎ ሄደን ከግራኝ በመዋጋት የሟቹን የክርስቶፎሮስን ደም እንድንበቀል ይርዱን ብለው ንጉሡን ከመለመን ባልደረሱ ነበር ።

ሁለቱም ወገኖች ድልን ወደየራሳቸው በመሳብ እንዳይመኩና እንዳይኩሩ እግዚአብሔር የድሉን ጸጋ ለሁለቱም በክርስቲያንነት ለተባበሩት ፖርቱጋሎችና ኢትዮጵያውያን የሰጠ ይመስላል ። በወፍላው ጦርነት በክርስቶፎሮስ ደጋማ መሪነት ግራኝ ተሸንፎ ቢሞት ኖሮ በወጣቱ መሪና በፖርቱጋሎቹ ዘንድ ትምክህትና ኩራት አድሮ የእንግዶቹና ያፄ ገላውዴዎስ ግንኙነት ከአሁን የተለየ ሌላ መልክ ሊይዝ ይችል ነበር ። ንጉሡም ለብቻቸው ከኢትዮጵያውያኑ ጋር አሸንፈው ግራኝን ገድለው ቢሆን ለተቀደሰ ተግባር ከሩቅ በመጡት እንግዶች ላይ መናቅ ሊደርስባቸው በቻለ ነበር ። የሆነ ሆኖ ታሪክ ነገሥቱ ከድሉ በኋላ የነበረውን ሲያብራራ «በዚያን ጊዜ ሠራዊቱ እንደ ጢስና እንደ ዓመድ ተበተኑ ። ከመካከላቸው ከሚስቱ ከድል ወንበራ ጋር ሆነው ከፍርሃት የተነሣ ወደ አትባራ ሸሹ ፣ የቀሩትም የሚዋጉበትን ሰይፍና ፈረስ እየተዉ በአንገታቸው ላይ ገመድ እያሠሩ ገቡ። በአደራ የነበሩትን ገደሉዋቸው ። ኢዮአራምንም ከገባ በኋላ የፈሰሰው የእሥራኤል ደም በከንቱ እንዳይቀር ገደሉት» ይላል (1) ።

አንድ ትልቅ መሪ ተመትቶ ሲወድቅ በተለይ የዚያን ዘመን ሠራዊት ተሰፋ ቆርጦ መሸሽ ፣ ሸሽቶ የሚያመልጥበት መሸሻ አገር የሌለው እንደ ዘመኑ እንዳገሩ ልማድ ባንገቱ ገመድ አሥሮ በትከሻው ደንጊያ ተሸክሞ በአሸናፊው ፊት ከመሬት ወድቆ ምሕረት መለመን የተለመደ ነው ። ስለዚህ አጠገቧ ፫፻ ፈረሰኞች ጠባቂ የነበሯት በኋላ ከጦርነቱ ተርፈው የተጨመሩላት የስሟ ትርጓሜ ድል ዙፋኗ ነው የተባለው ዋናዪቱና ስመ ጥር ሚስቱ ድል ወንበራ ሀብቷን እንደያዘች በአትባራ ወንዝ በኩል አድርጋ የመንገዱ ቊጥጥር ባልጠበቀበት ሰዓት ዞራ ተጠምዛ ወደ ሐረርጌ ገብታለች ። ከርሷም ጋር ግራኝን ተከትለው የመጡት የአዳልና የሱማሌ ወታደሮች ከነሹማምንታቸው እንደሚኖሩ የታወቀ ነው ። እነዚያ ብዙ ክርስቲያን እያሳደዱ የፈጁ እነ ቀጭኑ አቡበክር በእሁኑ ጊዜ ሞተው ይሆን ወይም አብረው ይሸሹ አይታወቅም ።

በአደራ የነበሩት ተገደሉ የሚለው አደራ (ወይም ደራ?) በሚባለው ወረዳ የሚ

(1) ወእሜሃ ተዘርዉ ሠራዊቱ ከመ ጢስ ወከመ ሐመደ እቶን ወቦ እለ ጐዩ እስከ አትባራ ምስለ ብእሲቱ ድል ወንበራ እምብዝኃ ፍርሃት ፤ ወቦ እለ ገብኡ ሐብለ እግሪሆሙ ውስተ ክሳዶሙ ኀዲገብአ ከመ ኢይትረሳዕ በቀለ እሥራኤል ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 95 ፤ ወበ እለ ቀተልዎሙ ለእለ ነበሩ በአደራ ። ለኢዮአራምኒ ቀተልዎ እምድኅረ

ጉኙ የግራኝ ወታደሮች ምናልባት እየተዋጉ ለመከላከል የፈለጉ ይሆናሉ ። ታሪከ ነገሥቱ በዚህም ላይ በሌላም ቦታ ምሕረት እየለመኑ ለገቡት ሁሉ ባባቱም በር ሱም በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ለበደሉ ሁሉ ሳይበቀል ምሕረት አደረገላቸው ይልና በነዚህ ውስጥ ኢዮአራም የተባለውን ብቻ ከገባ በኋላ የእሥራኤል በቀል እንዳይ ቀር ገደሉት ብሏል ።

ኢዮራም (ወይም ኢዮአራም) የተባለው የጸለምት ሹም ነው ። እርሱም በዋ ናው የጦርነት ወቅቶች እነዚያ ከሐዲዎች እንአዝማች ሐይቢ እነ አናንያ ያደርጉት እንደነበረው ገና አስቀድሞ ጌታውን ዓፄ ልብነ ድንግልን ከድቶ ወደ ግራኝ ዞሮ ባለሟል በመሆን ምሥጢር እየገለጸ የጠላትን ጦር እየመራ ንጉሡን እስከ ሽሹበት ተራራ ድረስ እያሳደደ ያጠቃቸው ነው ።

ዓፄ ልብነ ድንግል ለግራኝ ጋብቻውን እምቢ ብለው መከራ ያጸናባቸው ጊዜ ይኸንኑ ለመበቀል ኤሚር ኡመር በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ሰለዋ ሳሉ ወግቶ ብዙ ሠራዊት የፈጀባቸው ጊዜ እርሳቸው ሊማረኩ ሲሉ ለጥቂት ከትንሽ ወታደር ጋር አምልጠው ጭልምፍራ ከሚባለው ተራራ ላይ ሄደው ቢደበቁ ኢዮአራም የዚሁ የጸለምት ገገር ነበርና በሚያውቀው መንገድ የግራኝን ጦር እየመራ መጥቶ ከዚያም ወጥቶ አባሯ ቸዋል ። ይኸንኑ የተረከው ታሪከ ነገሥት «ወእምሀየኒ ካዕበ ሰደዶ ኢዮአራም በዓለ ሀገር ምስለ አሐዱ መለሳይ ፤ ከዚያም ያገሩ ጌታ ኢዮአራም ካንዱ እስላም ጋር አሳደዳቸው» ያለውን ማስታወስ ይበቃል (1) ።

ISIC

ይህን በመሰለ አኳኋን ከጠላት ጋር ተደርቦ ሲያጠቃ የኖረ በመሆኑ አሁን ግራኝ አህመድ በዘንተራ ዳገት ሞቶ የእስላሞቹ ሥልጣን በወደቀበት ሰዓት የሚሄ ድበት አጥቶ ቢገባም ምሕረት የማይገባው ነው ተብሎ ተገደለ ማለት ነው ። እንደ ዚሁም አንድ ስሙ ያልተገለጸ ኢትዮጵያዊ ሹም ግራኝና ፖርቱጋሎቹ በወፍላ (አሸንጌ) የተዋጉለት ቆስሎ በዋሻ የተደበቀውን ክርስቶፎሮስን በመማረክ ከእስላ ሞቹ ጋር ተባብሯል የተባለው በአዋጁ መሠረት ገብቶ ይቅርታ ተደርጎለት ሳለ ያለቃቸው የሞቱ ብቻ ሳይሆን የአሟሟቱ ጸጸት ከልባቸው ያልጠፋው ፖርቱጊ ዞች ከንጉሡ ፊት ዘወር ሲል በጩቤ ወግተው ገደሉት ። የርሱን አሟሟት ካስታን ሆዞ በመጽሐፉ ዘርዝሮ እንደጻፈው ታሪከ ነገሥቱም አልዘነጋውም "ለሁሉም ምሕረት ተደረገ ከኢዮአራም በቀር ምሕረት አግኝተው የገቡትን ማንም አልነካቸ ውም ውሻ እንኳን በመላሱ አልላሳቸውም" ካለው ከተል አድርጎ «ከተማሩት አንዱ ክፋቱ ወይም ወንጀሉ እስከ ደመናት ድረስ ከፍ ያለውን ከፖርቱጋሎቹ አንዱ ያለ ንጉሡ ፈቃድ ገደለው» ሲል የካስታንሆዞን አጻጻፍ ደግፏል (2) ።

(1) ባለፈው እንዳመለከትነው መለሳይ የሚለው አንዱን የግራኝን የጦር አለቃ ነው ። ግዕዝኛው ቃል የእስራኤል በቀል እንዳይቀር የሚለው የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ የእስራኤል ተወላጅነታ ቸውን ከማመን ጋር በምድያም ሰዎች የእስራኤልን ልጆች በቀል ተበቀልላቸው ብሎ ለሙሴ ያዘ ዘውን ተከትሎ በመጥቀስ ነው ፤ ዘኁልቁ ምዕ. 31 ቍ. 2

(2) ......... ወባሕቱ ፩ዱ እም እሉ ዘተለዓለት እከዩ እስከ ደመናት ቀተሎ ፩ዱ እም ሠራዊተ ብር ትጓል እንዘ ኢመፍቅዱ ለእለ ዝንቱ ማር ገላውዴዎስ ላዕሌሁ ሰላም ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 101 ። የፖርቱጋል ዝግንነት ምዕ. 24 ።

በኢጣልያ ወረራ ጊዜ አንዳንድ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የነበሩ በአሳባቸው የወደቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ተመልሶ የማይነሣ የተመሠረተው የኢጣልያ አገዛዝ የማይፈርስ እየመሰላቸው ወደ ኢጣልያ ባለሥልጣኖች እየገቡ ማዕር ግና ሹመት እያገኙ ያገለግሉ እንደነበረው በዚህም ጊዜ የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አባት ለግራኝ ገብቶ በሹመት በከበሬታ ተቀምጦ የግራኝን ልጅ ለመጠበቅ ሞግዚትነትን እስከ ማግኘት ደርሶ የነበረው የግራኝን ልጅ ለማስረከብ ፈቃዱ መሆኑንና ለርሱም ምሕረት እንዲደረግለት መልክተኛ ወደ ንጉሡ ላከ ። ካስታንሆዞ እንዳለው ምንም በሰውዬው ላይ ንዴት ቢኖርባቸው የግራኝን ልጅ ለማግኘት ሳይሆን ልጁ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በዚህ ጊዜ ስለአሳየው ታማኝነትና አገልግሎት ብቻ ላይ ገድሉት ቃል ሰጥተው የግራኝን ልጅ ይዞ ገባ ።

ይህ በዕርቅ የግራኝን ልጅ ይዞ የገባው የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አባት ምናልባት በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ አፍራ የተባለው ይሆናል ። እርሱም ከሌሎቹ ከዳተኞች ጋር ወደ ግራኝ ዞሮ ስለአገለገለ በግራኝ ፈቃድ እነዘርዓ ሠናይ ሐማሴንን እነ ተስፋዊ ሠራዬን የተሾሙለት ፖርቱጋሎች ራሱን ቆርጠው የላኩት ኑር የደሆኖን ወደብ የተሾሙለት እርሱም ባሕር ነጋሽ ተብሎ ተሾሞ ነበር (1) ። በዚህም ዓይነት አባቱ የግራኝ ባሕር ነጋሽ ሲሆን ልጁ ደግሞ ያፄ ገላውዴዎስና የንግሥት ሰብለ ወንጌል ባሕር ነጋሽ ነበር ማለት ነው ።

ማናቸውም የወረራና የነፃነት ቀን የታማኞችና የከዳተኞች መደብና የሚደርሳቸው ዕድል በየትም አገር ተመሳሳይ ነው ። በወረራ ዘመን ከዳተኞች በወራሪው አስተዳደር ጊዜ ከተደሰቱት ይልቅ ታማኞች በነፃነት ቀን የሚሰማቸው ደስታ የበለጠ ነው ። ደስታቸው ከነዚያ የበለጠ ወግና ታሪክ የያዘ ደስታ ነው ። በኢትዮጵያ ያሁኑ የግራኝ ወረራና የኋለኛው የኢጣልያ ወረራ የአስከተለው ሁሉ በብዙ ረገድ ተመሳሳይ መሆኑን ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው አሁንም ዓፄ ገላውዴዎስ ያሉበት ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. እና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት የ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ጊዜ የሚያሳየው መልክ አንድ ነው ። ወረራው የግራኝ በ፲፬ ዓመት ቢራዘም የኢጣልያው በ፭ ዓመት ቢያጥር ኢጣልያ ከባሕር ማዶ የመጣ የነጭ ዘር ቢሆን ግራኝ ከነጦሩ ከቅርቡ ከአዳልና ከሱማሌ ቢነሣ ዞሮ ዞሮ ሁለቱም ያው ጠላት ሆነው በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ያወረዱት እልቂት የሚመሳሰል ነው ።

በኢጣልያ የወረራ ዘመን ከሁለት ወንድማማች ወይም ከአባትና ከልጅ አንዱ ስደተኛ ወይም አርበኛ ሆኖ እናት አገሩን ሲያገለግል ሌላው ባንዳና የባንዳ ለወደቀውና ለስደተኛው መንግሥት ታማኝ ሆኖ ቀድሞ ዓፄ ልብነ ድንግልን በኋ ላም ንግሥት ሰብለ ወንጌልን ሲያገለግል የመጡትን ፖርቱጋሎች በምጥዋና በደባ ርዋም ተቀብሎ በማስተናገድ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል በማገናኘት ከዚያ ወዲህ

(1) ዓረብ ፋቂህ በባሴት ረኔ ትርጉም ገጽ 449 - 450

እስካሁን የተደረገውን ጦርነት ሁሉ በመካፈል ሲያገለግል አባቱ ከዳተኛ ሆኖ እስከ ግራኝ ሞት ድረስ አገልግሎቱን ለወገኖቹ ጠላት ያበረከት ነበር ማለት ነው ። ከዚህ በፊት በዚህ ዓይነት የራስ ወሰን ሰገድ ታማኝነትና መሥዋዕትነት የወንድሙን የወናግ ዣንን ከዳት የሠራዬውን የተስፋ ልዑልን ከፍተኛ ዠብዱ የዘመዱን የቴዎድሮስን አለመታመን የተመለከትነው ትዝ ሲለን የታሪክን መደጋገም እን መለከታለን ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ሲቋቋም ብዙ አገር የበደሉ ወይም ከኢጣልያ ሥር ሆነው ያገለገሉ የኢትዮጵያ ሹማምንት በአርበኛው ወይም በስደተኛው ዘመዳቸው ምክንያት ይቅርታ እንዳገኙ አሁንም ያባትዬው ኃጢአት በልጁ በባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አገልግሎት ምክንያት ተፍቆ ሥርየተ ኃጢአትን አግኝቷል ማለት ነው ።

ታሪከ ነገሥቱ ዓፄ ገላውዴዎስ ከግራኝ ጋር አብሮ ለሠራውና ለበደለው ሁሉ ምህረት ማድረጋቸውን ለበደለ የበደሉን ዋጋ በቅጣት አለመክፈላቸውን እያወደሰ «መሐሪ ወመስተሣህል ወኢይፈድዮ እኪተ ለዘአህሰመ - ይቅር ባይና መሐሪ ላጠፋ ብድሩን አልከፈለውም» በሚል አነጋገር አመስግኗቸዋል ። ይኸውም ጃንሆይ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ባደረጉት ንግግር በኢጣሊያኖች ላይ ያለፈ በቀል እንዳትመልሱ ብለው ሕዝባቸውን ካስጠነቀቁት ጋር ተመሳሳይ ነው ። ነገር ግን በዚያን ሰዓት ዓፄ ገላውዴዎስ ፣ በኢጣልያ ወረራ መጨረሻ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጠላት ጋር አብሮ በሠራው ላይ ተገቢ ቅጣት ያልፈጸሙበት ከርኅራኄው ውጭ ይኸን የመሰለውን የርኅራኄ አቅዋም ሲወስዱ በሁለቱም ዘንድ ያስተዳደርና የሰላም ፍለጋ ምክንያት እንደ አለበት አይካድም ።

ጠላት አገርን በወረረ ጊዜ ሁሉም ስደተኛ ፣ ሁሉም አርበኛ መሆን አይችልም የቤተ ሰብ ጣጣ የንብረት የሥጋዊ ምቾት ጉዳይ አለ ። በዚህ ሁሉ መካከል የጠላት ባለሥልጣን በየአገሩ ተበታትኖ እደጁ ደርሶ ታማኝነትን ግብርን በሰይፍና በጥይት በትር እየጠየቀ በሚያስገብርበት ሰዓት ከልብና ከመንፈስ ባይቀበለውም ስላገርና ስለወገን ሕይወቱን መሠዋት የሰቀቀው የቤተሰብ አባት እሺ ብሎ የአሸናፊን ጠላት ፈቃድ ይነስ ይብዛ መፈጸም ግዴታ ነው ።

ነገር ግን እንደነሐይቢ እንደነአናንያ ገና መንግሥት ሳይፈርስ ወደ ጠላት ዞረው የጠላት ባለሟል ሆነው መንገድ እየመሩ ምሥጢር እየገለጹ ባላገርን እያታለሉ ታማኝን በስለላ እየጠቆሙ ሰው ያስፈጁ እንደኢዮአራም ተከላካይ የወገን መሪ የተደበቀበትን ለጠላት እያሳዩ ያስፈጁ ምንም ምሕረት ስለማይገባቸው እነዚህን የመሰሉትን ዓፄ ገላውዴዎስ ከገቡ በኋላ ራሳቸውን እያስቆረጡ ቀጥተዋቸዋል ። የቀረውን ጅምላውን ግን ጥፋተኞቹ ከመብዛታቸው የተነሣ እነርሱን በሞት ልቅጣቢሉ ብቻቸውን ስለሚቀሩ መጥተው እየገቡ ይቅርታ ለጠየቁት ሁሉ የተረጋገጠ ጠባቂ እየሰጡ እንደ ማሩዋቸው ካስታንሆዞ ያረጋግጣል (1) ።

(1) የፖርቱጋል ዠግንነት ምዕራፍ 24 ገጽ 72

ISIC

ይኸው የዚያን ጊዜ ሁኔታ በኢጣልያ የወረራ ፍጻሜ ላይ ስለመጣ ከኢጣልያ ጋር አብሮ ለሠራውና ለበደለው ሁሉ ወርቃዊ አዋጅ ተብሎ የአብሮ ሠሪውና የባንዳው ኃጢአት ሁሉ በዚህ አዋጅ ተደምስሶ ከኢጣልያ ጋር የሠራው ሁሉ ጠቅላላ ምህረት እንዳገኘ ባፄ ገላውዴዎስም ዘመን ከግራኝ ውድቀት በኋላ ለየፋተኞች ያደረጉት ጠቅላላ ምህረት ተመሳሳይ ነው ።

የሆነ ሆኖ መደምደሚያውን በአገር የወረራ ዘመን ከጠላት ጋር ሆኖ ከመደሰት ከወገን ጋር ማዘን የተሻለ ነው ። ዳሩ ግን ይህ ትምህርት ራሳቸውን ለሚወዱ ተድላ ደስታ በማናቸውም ዓይነት ቢመጣ በየቀኑ ለሚፈልጉ አድር ባዮች ከባድ ትምህርት ስለሆነ ሁሉንም ሰው እንደጠባዩ ይቀበለዋል ።

## ምዕራፍ ፻፴

### ከግራኝ ሞት በኋላ የንግሥት ሰብለ ወንጌልና ያፄ ገላውዴዎስ መገናኘትና የፋሲካን በዓል አብሮ መዋል — የክርስቶፎሮስ ደጋማ የሙት ዓመት ተዝካር (፲፭፻፴፯ ዓ. ም. መስከረም)

ዓፄ ገላውዴዎስ ከግራኝ ጋር ሊዋጉ ሲመጡ እናታቸውን ሸዋዳ ላይ ትተዋቸው መምጣታቸውን እናስታውሳለን ። መቼም ከባላቸውም ከነክርስቶፎሮስ ደጋማም ጋር በዘመቱበት ጊዜ ሁሉ የግራኝን ተዋጊነቱን ብርታቱን ስለሚያውቁ ልጃቸው ገላውዴዎስ ግራኝን አለበት ድረስ ሊወጉት ሲሄዱ ምን ዓይነት ሥጋትና ጭንቀት እንደሚያድርባቸው ለማወቅ ቀላል ነው ። በወፍላ ግራኝ በርሳቸውና በክርስቶፎሮስ የተመራውን ጦር አሸንፎ እርሳቸውና ቤርሙዴዝ ከፊት የቀረው ጦር ከኋላ እየተዝረከረከ ቅጥ አጥቶ በላስታ በኩል አድርገው ወደ ሰሜን በተለይ ሸዋዳ ወደሚባለው በሽሽት ደርሰው ከልጃቸው የተገናኙበት ጊዜ አጭር ስለሆነ የግራኝ ኃይለኛነት የሽሽቱ የድንጋጤው የደጋማ ቆስሎ መማረኩ ሥቃዩ ሞቱ ሁሉ ሥዕሉ ከፊታቸው ማስታወሻው ከሕሊናቸው ላይ ገና ሊጠፋ አይችልም ።

አሁን ደግሞ ልጃቸው ገላውዴዎስ በዘንተራ ዳገት (ደንቀዝ) የግራኝን ጦር አሸንፈው ከድሉ ወሬ ጋር የባላቸውና የርሳቸው ኃይለኛ ጠላት የስመ ጥሩው ደመኛቸው ጭንቅላት ተቆርጦ በጦር ላይ እንደተሰካ ደርሷቸው ሲያዩት ያለፈውን ኀዘንና ጭንቀት ደምድሞ የሚያስረሳ ደስታ ገጥሟቸዋል ማለት ነው ። ያንድ ቀን ታላቅ ደስታ የብዙ ዘመን ኀዘንን ያስረሳል ።

የሆነ ሆኖ ንግሥቲቱ ግራኝ የሞተበትን የድሉን በዓል በደስታ ለማክበር በልጃቸው ጥሪ ከሸዋዳ ወደ ደምቢያ ሲሄዱ እነዚያ ከጦርነቱ በፊት ይጠበቁ የነበሩት የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ንግሥቲቱ ደርሰው ንግሥቲቱ በራሳቸው ሰዎችና በፖርቱጋሎቹ ታጅበው እንዳማረባቸው ወደ ልጃቸው መጥተው በደስታ ተገናኙ (1) ።

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 24 ገጽ 71

ስለንግሥቲቱና ስለ ገላውዴዎስ የዚህ ቀን ግንኙነት ካስታንሆዞ የጻፈው ትንሽ ነው ። ታሪከ ነገሥቱ በፍጹም አላወሳውም ። ከሁለቱ ይልቅ ቤርሙዴዝ ትንሽ ሰፋ አድርጎ እንደዚህ ይላል «በዚህ ሥፍራ (1) ሁለት ወር ቆየን ፤ በዚህ ጊዜ ንጉሡ ለናታቸው የድሉን ወሬ ላኩ ፤ እናትየዋ የነበሩት ከኛ ያንድ ቀን መንገድ ርቆ ነው (2) ። ይኸን አስደሳች ድል አብረን እንድናከብር ሲሉ ንግሥቲቱ እንዲመጡ ለመኑዋቸው . . . . . . ። ንጉሡ ለኔ ሳያስታውቁ ንግሥቲቱ ወደ ሠፈር ለመድረስ ገና አንድ የመንገድ ርቀት ሲቀራቸው በፈረሰኞቻቸው ታጅበው ሄደው ተቀበሏቸው ። ከሠፈራችን የአንድ ቀስት ውርወራ ርዝማኔ ባለው ንግሥቲቱ በሚያልፉበት መንገድ ላይ የሐር ልብስ ተጋርዶ ዋጋው ከፍ ከፍ ያለ ሥጋጃ ተነጥፎላቸው ነበር ።

ከደረሱ ዠምሮ ስምንት ቀን ሙሉ ለሰው ሁሉ መብልና መጠጥ እየተሰጠ ሲበላ ሲጠጣ ሰነበተ« (3) ።

በዚህ ዓይነት ደስታ እናትና ልጁ ተገናኝተው ደስታቸውን ሲያዩ ከፍተኛ ወንጀል ለሠራው ቅጣት ለቀረው ምሕረት ሲያደርጉ ሰነበቱ ካለ በኋላ በበኩሉ ካስታንሆዞ «ጊዜው የሁዳዴ ጾም ስለነበረ በጾሙና በሰሙነ ሕማማት መጨረሻ ዓርብ ከስቅለት ዠምሮ እስከ እሁድ ትንሣኤ የተደረገውን የጾሙን የጸሎቱን የንስሐ አሰጣጡን የስግደቱን የማኅሌቱን የቅዳሴውን ዓይነት ካገሩ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ጋር እያነጻጸረ ይተርክና የቅዳሚ ሥዑር ለት ሴቶቹ በወይራ ቅጠል (ዘንባባ ወይም ቁጠማ ?) የተሠራ መስቀል በራሳቸው ላይ አድርገው ወንዶቹ የሰሌን ዝንጣፊ ይዘው ወደ ቤታቸው እንደሄዱ ፣ የትንሣኤ እለት (እሑድ ሌሊት) ብዙ የጧፍ መብራት ተይዞ ዑደት ሲደረግ ፖርቱጋሎቹ ሁሉ መሣሪያቸውን እንደታጠቁ አብረው ዑደት ማድረጋቸውን በዚያን ጊዜ ጠበንጃዎች ከዓረቦቹ የተማረኩት መድፎች እየተተኰሱ ፖርቱጋሎቹ ለበዓሉ ተስማሚ የሆነ የጨዋታ እሳቶች እየተኰሱ ንጉሡን በማስደሰት ትልቅ በዓል መታየቱን ይገልጻል (4) ።

ISIC

በዚህ ዓይነት የቤተ ክርስቲያኑም ሆነ የቤተ መንግሥቱ የአለባበሱም የአቀማመጡም የአበላሉም ወግና ሥርዓት የአውሮፓዎቹ የፖርቱጋሎቹ የአፍሪካዎቹ የኢትዮጵያውያኑ የተለያየ ቢሆንም በክርስቲያንነት ፍቅር ተጠምደው ላንድ ዓላማ ደማቸውን አብረው ስለአፈሰሱ ሁለቱ ወገኖች ይኸን የ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ፋሲካ በደስታ አክብረው ዋሉ ።

(1) ደምቢያ ማለቱ ሳይሆን አይቀርም

(2) ከሸዋዳ ንጉሡ እስከ አሉበት እስከ ደምቢያ ግዛት ካንድ ቀን መንገድ ይበልጣል ነገር ግን ቀደም ብለው ንግሥቲቱ ከሸዋዳ ወደ ደንቀዝ ወይም ወደ ደምቢያ ቀረብ ብለው ሠፍረው ሰንብተው ይሆናል ።

(3) Hist. du Christ.......... ገጽ 176

(4) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕ. 25 ። ጠበንጃና መድፍ ተተኰሱ የሚለው ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ብሎ ቀዳሲው ቄስ ለመዠመሪያ ጊዜ የክርስቶስን ትንሣኤ በሚያበስርበት ጊዜ ይሆናል ።

መቼም ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ገላውዴዎስ ይኸን የመሰለ የደስታ ፋሲካ ካዩ ፲፭ ዓመት ሆኗቸዋል ። ግራኝ አህመድ ከተነሣበት ከ፲፭፻፲፱ ዓ. ም. ጀምሮ በተለይ ከሽምብራ ኩሬው ጦርነት ወዲህ በየተሰደዱበት ወረዳ በዋሻና በጫካውም ቢሆን ልደትንም ጥምቀትንም ቢሆን ማክበር እንደማያስታጉሉ ፋሲካንም ባለፈው በያመቱ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ያከብሩት የነበረው ካሁኑ የተለየ በኀዘን ፣ በጸጸት ፣ በሥጋት የተከበበ ፋሲካ እንደሚሆን አይጠረጠርም ። የሆነ ሆኖ በዚህ ዓይነት የፋሲካ በዓል ካለፈ በኋላ ንጉሡ በግንቦት ወር በዚሁ በጣና ባሕር ቀድሞ ከነበሩበት ሠፈር አለፍ ብለው ለርሳቸውና ለናታቸው ከተማ ከአሠሩ በኋላ ጭፍሮቻቸውን በዙሪያው አገር ሲመሩ ለፖርቱጋሎችም ከርሳቸው ከተማ የሁለት ጥይት ተኩስ ያህል የሚርቅ የከተማ ክፍል እንደመሩዋቸው በዙሪያውም ያለው የገጠር ባላገር እስከሚተርፋቸው ድረስ ለነርሱ ማር ቅቤ የሥጋ ከብት ለበቅሎና ለፈረሶቻቸው ስንዴና ገብስ እንዲሰጣቸው መታዘዙን በዚህ ዓይነት የክረምቱ ወራት ካለፈ በኋላ በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ (1) ክርስቶፎሮስ በሞተበት ቀን ንጉሡ ግሩም በሆነ አኳኋን ተዝካር እንዳወጡለት ፣ የተዝካሩ ዕለት ፳፱ ካህናትና መነኰሳት ለፍታት እንደተሰበሰቡና በዙሪያው የሚገኙት ፷ሺ የሚሆኑ ድሆች በለፈፉ መጥተው በድንኳን ውስጥ ምግብና ልብስ እንደታደላቸው ካስታንሆዞ ይተርካል (2) ።

ISIC

ምዕራፍ ፻፴፩

የሚጉኤል ደ ካስታንሆዞና የሃምሳ ፖርቱጋሎች ወደ ሕንድ መመለስ (፲፭፻፴፯ ዓ.ም.) — ዓፄ ገላውዴዎስ ስለካስታንሆዞ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ ።

የወታደር ጸሐፊ የሆነው ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ከቤርሙዴዝና ከታሪክ ነገሥቱ በተሻለ አኳኋን በዚሁ ጣና ባሕር አጠገብ ንጉሡና እናታቸው በሠፈሩበት ሥፍራ በመስከረም ፩ ቀን የሚውለውን የዘመን መለወጫ በዓል ይጠቅስና በመስከረም ፲፮ ቀን የሚደረገውን የደመራ በዓል ያመለክታል ። ንጉሡ ባንድ ቤት ውስጥ ሆነው ከውጭ ማንም ሊያያቸው በማይችል እርሳቸው ግን ሁሉንም ለመመልከት በሚችሉበት መስኮት ላይ ሳሉ አለቃው በየፈረሱ ጭፍራው በእግሩ ሆኖ ችቦ እያበራ (3) ቀጥሎ ሴቶቹ ሁሉ በእጃቸው የጧፍ መብራት ይዘው እየዘፈኑ ማለፋቸውን ካስረዳ በኋላ ላገር ጉብኝትና የተረፈ የግራኝን ጦር ለመቃረም ከጣና ባሕር

(1) ክርስቶፎሮስ ከወፍላ ጦርነት ላይ ተማርኮ የተገደለው በ፲፭፻፴፭ መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ ስለሆነ አሁን የሙት ዓመቱን ተዝካር ደግሰውለታል ማለት ነው ። ካስታንሆዞ በአውግስት (ነሐሴ) ያለው በመስከረም ማለቱ እንደሆነ አይታወቅም ።

(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ምዕራፍ 25 - 26

(3) በደመራው በዓል ጊዜ የሚበራውን መሆን አለበት ፤

ዳር ወደ ኤርትራ ባሕር አቅጣጫ በሠራዊታቸው እንደታጀቡ በጥቅምት ወር ጉዞ መጀመራቸውን የተከተላቸው የሕዝብ ቊጥር በግምት ፩፻፫ ሲሆን ከዚሁ ተዋጊው ወታደር ፪፻ ፈረሰኛ ፳፻ እግረኛ መሆኑን ያመለክታል (1) ።

ከዚህ እያይዞ የስምንት ቀን ጉዞ ሲያደርጉ በየመንገዱ የግራኝን ትራፊ ጦር ሲያስወጉና ሲያሳምኑ በየአገሩ ላይ ግማሾቹን እየሻሩ ግማሾቹን እየሾሙ አልፈው ካንድ የተቀጣጠለ ተራራ መድረሳቸውን በዚያም ፲፱ ከዓለት ደንጊያ ተፈልፍለው ከተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ካሉበት አገር (ላሊበላ) ደርሰው ከመኖኮሳቱ ጋር መገናኘታቸውን ከዚያ አልፈው ያርተፉ ሜዳ (2) ድረስ መሄዳቸውን በዚሁ በያርታፋ ሳሉ ራሱ ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞና ሃምሳ የሚሆኑ የፖርቱጋል ወታደሮች (3) ወደ አገራቸው ለመመለስ ንጉሡን ፈቃድ መጠየቃቸውን ራሱ ካስታንሆዞ ጽፎአል ።


ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ከክርስቶፎርስ ደጋማ ጋር መጥቶ እስከ ግራኝ ሞት ድረስ በተደረገው ጦርነት ሁሉ ሲዋጋ ከሁለት ላይ መቊሰሉን በተለይ ከሁለት እንዳቸው የቆሰለው ቊስል አልድን ብሎ ስለአሰቃየው ፪ኛም ግራኝ ሞቶ ንጉሡ መንግሥታቸውን ስለአቆሙ የመጣበት ፍሬ ነገሩ እንደተፈጸመ በመረዳት ደግሞ በኢትዮጵያ ቢቆይም እንዱ ከንዱ ሽባ ሆኖ ለማገልገል ባለመቻሉ ይኸን ሁሉ ምክንያት በማቅረብ ምጥዋ በዚህ ወር በሚገኘው መርከብ ተሣፍሮ ወደ አገሩ ለመመለስ የንጉሡ ፈቃዳቸው እንዲሆን ጠየቃቸው ።

ISIC

ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ ፩ኛ መንግሥታቸው በሙሉ ባልተቋቋመበት ሰዓት ፪ኛ የመንግሥቱ ሀብት ተዘርፎ ያላቸውንም ትንሽ ሀብት ላለፈው መንግሥታዊ ተግባር በችሮታ ጨርሰው ግምጃ ቤታቸው በተራቆተበት ሰዓት እርሱን ለመሰለ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ተመጣጣኝ የሆነ ችሮታ ሳያደርጉለት ወደ አገሩ መመለሱ እንዳሳዘናቸውና ትንሽ ሀብትና ወርቅ ካገር ላይ እስኪሰበሰብና እስኪገባ እንዲቆይ አባብለውት ባንድ ወገን ደግሞ ባገሪቱ ሐኪም ስለሌለ በቊስሉ ብርታት የተነሣ የርሳቸውን ችሮታ በመጠበቅ በሕይወቱ ላይ አንዳች ነገር ቢደርስ የሚያዝኑበት በመሆኑ ብቻ እሺ ብለው በኀዘንና በጸጸት እንዳሰናበቱት ፤ ሲያሰናብቱት ከራሳቸው አንድ ፈረስ ሁለት ጥሩ ጥሩ በቅሎዎች ሰጥተው በወርቅ አበባ የተጠለፈ አረንጓዴ የከፋይ ካባ ሸልመው በመንገድ እየቀለበ የሚሸኘው መሪ አድርገው ደግሞ ለስንቅ እንዳይቸገር ከዚያው ከባዶው ግምጃ ቤታቸው ሐያ ወቄት ወርቅ ሰጥተው ለፖርቱጋል ንጉሥ አንድ ደብዳቤ አሲዘው በሚያሳዝንና በፍቅር ሁኔታ እንዳሰናበቱት ይገልጸል ።

ዋናው ደብዳቤ ዓፄ ገላውዴዎስ ለሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለጳውሎስ ፫ኛ ስለ ቤርሙዴዝ ከጻፉት ደብዳቤ ጋር (BIBLEOTECA VATICANA) በሚባለው

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕራፍ 26 - 27 ፤
(2) ያርታፋ በትግሬ ግዛት ውስጥ ወደ ቀይ ባሕር የሚጠጋ ወረዳ ይመስላል ።
(3) ከምጥዋ አዲስ የመጡት ይሁኑ ወይም የቆዩት አይለይም ።



የጥናው ደብዳቤ ትክክለኛ የፎቶ ግልባጭ ፤

በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ቍጥር 75 ተሰጥቶት ከተቀመጠው ጋር እንደዚሁም ንጉሡ ስለሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉት ታሪካዊ ያደራ ደብዳቤ አብሮ ይገኛል ። እርሱንም በፎቶ ግልባጭ አስነሥቼው ስለነበረ ቃሉ በግዕዝ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

«በስመ እግዚአብሔር ሥሉስ ዘኢይትፈለጥ ዘይሬኢ እንተ አፍአ ወይፈትን እንተ ውስጥ ዘያደክም ለጽኑዕ ወያጸንዖ ለቅጥቁጥ (1) ። ተፈነወት ዛቲ መጽሐፈ መልእክት እም ኀበ ንጉሥ ገላውዴዎስ ወልደ ወናግ ሰገድ ንጉሥ ወልደ ናዖድ ንጉሥ ወልደ እስክንድር ንጉሥ ወልደ በእደ ማርያም ንጉሥ ወልደ ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ ወልደ ዳዊት ወልደ ሰሎሞን ንጉሥ ነገሥተ ኢትዮጵያ ለሁሉ ላዕሌሆሙ ሰላም ።

ትብጻሕ ኀበ ዮሐንስ ንጉሠ ብርትጋል (2) መፍቀሬ እግዚአብሔር ወመፍቀሬ ሃይማኖት ወልደ ንጉሥ ዘአማኑኤል ርቱዐ ሃይማኖት ። ስማዕ በእንተ ሚካኤል ገብርከ ዘመጽአ ኃቤነ ዘፈነዎ ገበርነ ምስለ ክርስቶቡ ደጋማ የደጂ አዝማች (3) ከመ ደርድኡነ ጊዜ ጸብእ ። ወዝንቱሰ ሚካኤል ተግሀ ጥቀ ለኢትዮጵያ (4) ወተቃተለ ምስለ እስላም በእንተ ክርስቶስ እንዘ ይሜጡ ነፍሶ እስከ ተሰብረ ፀጋማይ እዴሁ በነፍጥ ወበፈቃደ እግዚአብሔር እምድኅረ ሐይወ እምደዌሁ ናሁ ፈኖናሁ ኀቤከ ። ወእንተኒ ግበር ሎቱ ሠናያተ ተዘኪረከ ፍቅረ ክርስቶስ ወፍቅረ ዚአነሂ ። ውእቱሰ ፈጸመ መልእክተከ ከመ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ወጳውሎስ ልሳነ ዕፍረት ። ወበእንተዝ ትግሀቱ ለሚካኤል ክስተሆዝ (ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ) ዘፈኖከ ወአሊከ ከመ ይትራዳእ ወገብረ በከመ አዘዝኮ ወኢያብጠለ መልእክተከ ። ወዘንተኒ ተዘኪረከ ግበር ሎቱ ዘሐለየ ልቡ ዘኢጸሐፍኖ ውስጥ ዝንቱ መጽሐፈ መልእክት ። ወንሕነኒ ሰበ ንሰምእ ዜና ዝንቱ መልእክት ንትፌሣሕ ብከ ወይከውን ፍጹመ ፍቅርነ በዝንቱ ግብር» (5) ።

በደብዳቤው ላይ እንደተለመደ የዘመኑ ጸሐፊ ቀንና ዓመተ ምሕረት አላደረገበትም ። ይሁን እንጂ ዓመተ ምሕረቱ ፲፭፻፴፮ መሆኑ አያጠራጥርም ። ከንጉሡ የተሠናበተው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የሚውለውን የልደትን በዓል ውሎ ስለሆነ ከምጥዋ በጀልባ የተሣፈረው እንደ አው. ቍጥር የካቲት ፲፯ ቀን መሆኑን ራሱ ስለሚያረጋግጥ የተጻፈበት ወር የጥር ወር ሳይሆን አይቀርም ። ንጉሡ ፍጹም ሃይማኖተኛ መሆናቸውን ወይም ከዮሐንስ ፫ኛ ከፖርቱጋል ንጉሥ በዝምድና ያሣሰራቸው የክ

ISIC

(1) የዳዊት መዝ. 75 ቍ. 11
(2) ፖርቱጋል ለማለት ነው ፡
(3) እኛን ለመርዳት ከክርስቶፎሮስ ጋር ለመጣው ለሚካኤል (ሚጉኤል) የደጃዝማችነት ማዕርግ ሰጠነው ለማለት ወይም ደጃዝማች የሚሉት ክርስቶፎሮስን ይመስላል ።
(4) በዚያን ጊዜ የእ ሳድስ ቅጥሉ ወደ ግራ የነበረው ዛሬ ወደ ቀኝ መሆኑን ከደብዳቤው ሥዕል ተመልከት ።
(5) የዚችንም ደብዳቤ የፎቶ ግልባጭ አልበር ካሚረር La mer Rouge - l'Abissinie et l'Arabie. በሚል አርእስት ባሳተመው መጽሐፉ በመዠመሪያው ክፍል ገጽ 49 ላይ አትሞታል ።

ርስትና ፍቅር መሆኑን ለማስረዳት ከደብዳቤው እናት ላይ የክርስቶስን ሥነ ስቅ
ለት አስለውበታል ።

ከደብዳቤው መዠመሪያ ላይ በዝርዝር ከታች አባቶቻቸውን እነዘርዓ ያዕቆ
ብን እነሱም ከላይ የጿኤል ነገሥታት የዳዊትና የሰሎሞን ዘር መሆናቸውን ጠቅሰ
ዋል ። የደብዳቤው አሳብ በትትክክል ስለሚታወቅ በሙሉ ወደ አማርኛ ለመተር
ጐም አስፈላጊ አልመሰለኝም ። ዋናው ፍሬ ነገር በክርስቶፎሮስ ደጋማ አዝማች
ነት እኛን ለመርዳት የመጣው ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ለኢትዮጵያና ለክርስቶስ
ሲል ግራ እጁ እስኪሰበር ድረስ ከእስላሞች ጋር በመዋጋት ሕይወቱን የሰጠና እን
ደሚገባው የተዋጋ ሰው ስለሆነ ካንተ ተልኮ የመጣበትን ዓላማ አንድም ሳያስቀር
የሐዋርያት ሹምን የጴጥሮስን ፤ ንግግሩ የሚጥመውን የጳውሎስን ምሳሌ በመከተ
ተል የተላከበትን ዓላማ የፈጸመ ሰው ነውና በዚህ ደብዳቤ ያልገለጽነውን ልቡ
የሚመኘውን "ሹመትና ሽልማት" ፈጽምለት የሚል ያደራና የምስክር ወረቀት
ነው ።

ይኸንንም ለመጻፍ ያሳሰባቸው ባለፈው እንዳነበብነው ከሩቅ አገር ባሕር
አቋርጦ ከጠላታቸው ጋር በመዋጋት ክንዱን በጥይት በትር ላጣው ሰው የሚመኙ
ትን ችሮታ ለጊዜው መስጠት ስለተቸገሩ ወይም የሰጡት ለሥራው አገልግሎት
በፍጹም በቂ አለመሆኑን በመረዳት የፖርቱጋል ንጉሥ አሟልቶ እንዲሰጠው
ለማሳሰብ ነው ።

ISIC

መጠሪያ ስሙን ባገሩ ቋንቋ ሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ የሚባለውን እርሳቸው
ወይም የእርሳቸው ጸሐፊ በኢትዮጵያ አጠራር ሚካኤል ብለውታል ፤ ካስታንሆዞ
ለማለትም ስለአዳገተ ከስትሆዝ ብለውታል ። መቸም የሰው ሁሉ አጠራር እንዳ
ገሩ እንደፈደሉ መሆኑን ከዚህ በፊት ያመለከትሁ ይመስለኛል ። እኛ ከግሪኮች
ወርሰን ሚካኤል የምንለውን ፖርቱጋሎች ሚጉኤል ይሉታል ። አሁንም ይኸንኑ
የሚካኤልን ሥያሜ ፈረንሳዊ ሚሸል ሲል እንግሊዙ ማይክል የስላቭ ወገን ደግሞ
ሚካኢሎቪች ይላል ።

እንደዚሁም ከርሱ ጋር ሊሄዱ የተነሡትን ሃምሳ የፖርቱጋል ተወላጆች ከኔ
ጋር ወደ ዳሞት ዘምታችሁ የወርቅ ግብር ከተሰበሰበ በኋላ ለአገልግሎታችሁ የሚ
ገባ ስጦታ ሰጥቼ ላሰናብታችሁ ብለው አባብለዋቸው ሳለ እነርሱ ግን ወደ አገራ
ቸው ለመሄድ ያላቸውን ምኞት በማጥበቅ ልመናቸውን ስለ እጸኑ ንጉሡ ገላውዴ
ዎስ ቢቸግራቸው ከቤተ መቅደስ የወርቅና የብር ዕቃ ከናታቸውና ከዘመዶቻቸው
የዕንቍና የአምባር ጌጥ አሰብስበው እንደሰጡዋቸው ፖርቱጋሎቹ ግን ይኸን በመ
ሰለ አኳኋን የቀረበላቸውን ስጦታ ለመቀበል ያልተደሰቱ መሆናቸውን ያመለከ
ታል ።

የሆነ ሆኖ በዚህ ዓይነት ካስታንሆዞ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ በፍጹም ፍቅርና መተ
ሳሰብ ከዓፄ ገላውዴዎስ ተሰናብቶ ወደ ምጥዋ ሄደ ። በዚያም የተርከ መርከቦች
እንዳያገኙዋቸው እየተጠነቀቁ ከባሕር ዳር ሆነው ሲጠባበቁ ዲዮጎ ዲ ሬይኖዞ
ትንሽ ጀልባ ይዞ መጥቶ በመድፍ ተኩስ ምልክት ጠርቶ ተገናኛቸው ፤ የመጣችው

ጀልባ ሁሉን ለመያዝ ባለመቻሏ ካስታንሆዞ ግን የዓፄ ገላውዴዎስን ደብዳቤ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዮሐንስ የያዘ በመሆኑ በቅድሚያ ተሳፍሮ ለቀሩትም ለሕንድ አገረ ገዥ አሳስቦ ሌላ መርከብ እንደሚያስልክ ተስፋ ሰጥቶ እንደ አው. ቀ.ጥር የካቲት ፲፮ ቀን ፲፭፻፺፫ ዓ. ም. በመርከብ ከምጥዋ ተሳፍሮ ሄዶ በሚያዝያ ፲፱ ቀን ሕንድ መድረሱን ይገልጽና እዚህ ላይ ታሪኩን ደምድሞ ይዘጋል (1) ።

ሙሴ ኢኖ ሊትማን ካስታንሆዞ ከምጥዋ ሕንድ ከሄደ በኋላ ከሕንድ ወደ አገሩ ወደ ሊስቦን ገብቶ ስለ አገልግሎቱ እንደ አው. ቀ. በ፲፭፻፺፬ ዓ. ም. ያንድ መርከብ ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ወደ ሕንድ አገር እንደገና ተልኮ እንደነበረ ያረጋግጣል (2) ። ምናልባት ይኸንንም ከፍተኛ የመርከብ ሹመት ለማግኘት ከረዱት ምክንያቶች ዋነኛው ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ ለዮሐንስ ፫ኛ የጻፉለት ያደራ ደብዳቤ ይሆናል ።

በዚህ ዓይነት ፍቅርና በወዳጅነት መንፈስ በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካከል የተመሠረተውን ዝምድና ወደፊት ቤርሙዴዝ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ካልሆንሁ ብሎ ከግራኝ ሞት በፊት ከዚህ በፊት ሸዋዳ ላይ ይጨቃጨቅ የነበረውን አሁንም ወደፊት በዚሁ ምክንያት በሚያመጣው ጠብና ክርክር ሲያፈርስ በኀዘን እንመለከታለን ። ይሁን እንጂ በዝርዝር አገልግሎት የተመራን እንደሆነ ኢትዮጵያ በማናቸውም ረገድ በጠቅላላው የፖርቱጋል መንግሥትና የ፬፻ ፖርቱጋሎች ባለውለታ ስትሆን በዝርዝር የጦሩ መሪ የክርስቶፎሮስ ደጋማ ፥ ርዳታውን ሄዶ ያመጣው የዮሐንስ ቤርሙዴዝ በውጊያ ጊዜ ግራ ክንዱን ከማጣት ጋር ለዚህ ዓይነተኛ ታሪክ የጽሑፍ ቅርስ የተወልን የሚጉኤል ደ ካስታንሆዞ ባለውለታ ነች ። እነዚህና በጽሑፉ ላይ ሲዋጉ ለሞቱት ሁሉ የመንገድ መታሰቢያ ሊሰጣቸው ይገባል ። ለክርስቶፎሮስ ደጋማ ግን ተማርኮ በሥቃይ በሞተበት ቀበሌ በዚሁ በወፍላ ወይም በኮረም ደንበኛ ሐውልት ይገባዋል ። በዚህ አድራጎት ኢትዮጵያ ውለታ የማታስቀር አገር መሆኗን ታስመሰክራለች ። ይኸንንም ሳሳስብ በአሁኑ ጊዜ በሞዛምቢክና በአንጎላ ምክንያት በፖርቱጋልና በአፍሪካውያን መካከል ያለውን የፖለቲካ መቃቃር ሳልዘነጋ ነው ። ነገር ግን ለባለውለታዎቹ መታሰቢያቸውን አቁመን የዛሬዎቹ የፖርቱጋል መሪዎች ለወገኖቻችን አፍሪካውያን ነፃነት መከልከሉን ከጸኑበት በፖለቲካም ቢያስፈልግም በጦር ኃይል መቃወም ይቻላል ።

(1) የፖርቱጋሎች ዝግንነት ምዕራፍ ፹፯ - ፹፰ በነአቶ ዮና ቦጋለ ትርጉም
(2) የፖርቱጋሎች ዝግንነት መግቢያ ገጽ ፲፩

# ፮ኛ ክፍል
# የሃይማኖት ክርክር

## ምዕራፍ ፻፴፪
## የክርስትና ሃይማኖት መመሥረት — በዓለም ላይ የድርጅቱ አከፋፈልና የጠቡ ምክንያቶች ።

የፖርቱጋሎቹን ርዳታ ባመጣው በቤርሙዴዝና በዓፄ ገላውዴዎስ መካከል ወደ ተነሣው የሃይማኖት ጠብ ከመግባታችን በፊት በቅድሚያ ስለክርስትና ሃይማኖት አመሠራረትና ስለ አከፋፈሉ ወይም ስለ ጠቡ ምክንያት አሁን በዚህ ምዕራፍ ባጭሩ ማመልከት የተገባ ነው ።

ወንጌላውያኑ እንደጻፉት ክርስቶስ በናዝሬት ተወልዶ አድጎ በዚያው በእስራኤል አገር ክርስትናን አስተምሮ ሲሞት ከመቃብር ተነሥቶ ይኸን የክርስትና ሃይማኖት እየዞሩ እንዲያስተምሩ ለወገኖቹ ለሐዋርያት ነግሮ እርሱ ወደ ሰማይ ከዓረገ ወዲህ ሐዋርያቱና ሰማዕታቱ እየዞሩ ሲያስተምሩ በጉባኤው እርስ በርሳቸው ተሰብስበው ሲነጋገሩ አባባቸው አዲሱን የክርስትና ሃይማኖት ባንድ የትምህርት መሥመር ማስተማርና ማስፋፋት ነበር ። ስማቸውም[sic]ክርስቲያን (የክርስቶስ ተከታይ) ብቻ ነበር እንጂ ካቶሊክ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ፕሮቴስታንት የሚባል አልነበረም ። በነርሱም ዘንድ ከወደ መገመሪያው ዘመን ላይ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ ገምሮ በ፫ መቶ ዓመት ውስጥ የክርስቶስ ባሕርይ እየተመረመረ ፩ ባሕርይ ነው የለም ፪ ነው ፤ ማርያም የአምላክ እናት መባል ይገባታል አይገባም የሚሉ ጠብና ክርክር አልነበረም ። በዚህ ፈንታ በያለበት በእስራኤል አገር በግሪክ አውራጃ በሮማ በዛሬው በቱርክ ግዛት ያን ጊዜ የቈስጥንጥንያ ግዛት በሚባለው ሰማዕታቱ እየዞሩ አዳኙነቱን ብቻ እያስተማሩ በዚህ የተነሣ ከአረመኔዎች ነገሥታትና ሕዝብ የሚያደርስባቸውን ስደትና መከራ በሚያስደንቅ ጽናትና ትዕግሥት ተሸክመው እስከ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ ደረሱ ። ቆስጠንጢኖስ የሮማ ግዛት ንጉሠ ነገሥት የነበረበት ጊዜ እንደ አውሮፓ አቈጣጠር ፫፻፮ - ፫፻፴፯ ዓ. ም. እንደ ኢትዮጵያ ፫፻፬ - ፫፻፴ ነው ። እንግዲህ ከ፫፻ ዓመት ይበልጥ ክርስቲያኖቹ እላይ እንዳልነው በመካከላቸው የእምነትና የምርምር የመለያየት ጠብ ሳይኖርና ሳይለያዩ በፍቅርና በመተሳሰብ ኖሩ ። ከቆስጠንጢኖስ በፊት በነበሩት አረማውያን ነገሥታት በኔሮን በነመክስምያኖስ በነዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ክርስቶስ የአምላክ ልጅ አዳኝ ነው ብለው ስላስተማሩ ለቀድሞው አረማዊ ሃይማኖት ለነጁፒተር ለነቬስታ ቀናዕያን ከሆኑት ዘንድ በመጣባቸው ስደትና መከራ ሥቃይ በርከቶባቸው ነበር ። አሁን ግን ቆስጠንጢኖስ በሰፊውና በታላቁ በሮማ ግዛቱ ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉ በነፃነት ሰው ሁሉ የወደደውን ሃይማኖት ይከተል የሚል አዋጅ በዛሬው የኢጣልያ አገር በተ

ሰይ ሚላኖ ላይ በ፫፻፲፫ (፫፻፭) ዓ. ም. ያደረገ ጊዜ ክርስቲያኖች እንደልብ ለማስተ ማርም ለመሰብሰብም ነፃነት አገኙ ። ይህ ነፃነት ያበለፀ ብዙ ተከታይ አበረከተላ ቸው ። ተከታይም ሲበረክት እንደደረጃቸው ሹመት አበል መያልያል ፣ የሹመት አገር መከፋፈል በየከተማው መመደብና ሥፍራም መለየት ስለአስፈለገ በአራቱ ወንጌላውያን የመደብ ቊጥር ከዚህ እንደሚከተለው ተደለደሉ ታወቀ ።

፩ኛው. የሮማ የቤተ ክርስቲያን መሪ የጴጥሮስ ተከታይ መቀመጫው ሮማ (ኢጣ ልያ)

፪ኛው. የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪ የማርቆስ ተከታይ መቀመጫው እስ ክንድርያ (ግብፅ)

፫ኛው. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪ የዮሐንስ ተከታይ መቀመጫው ኤፌሶን ቀድሞ (ግሪክ አሁን ቱርክ)

፬ኛ. የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪ የጴጥሮስ ወንበር (ድጋሚ) መቀመጫው አን ጾኪያ ይሁን ብለው ወሰኑ ። በኋላ ግን ቆስጠንጢኖስ የሚቀመጥበትን የቊስ ጥንጥንያ ከተማ ለማክበር ሲባል የኤፌሶኑ የሊቀ ጳጳስናው መንበርኛ ክብር ከኤፌሶን ወደ ቊስጥንጥንያ ዞረ ።

እንደዚህ እያደረጉ በበኩላቸው ሊቃነ ጳጳሳቱ ከዚያ በታች ላለው የጳጳስነት የኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ ለየከፍተኛ የቤተ ክህነት ሰዎች እየሰጡ በያለበት በሹ ሽር በድልድል አከፋፈሉ ። ለመዠመሪያው ጊዜ ከሊቃነ ጳጳሳቱ ሁሉ የሮማው ቤተ ክርስቲያን አለቃ የበላይ እንዲሆን ሁሉም ተስማምተው ነበር (፩) ።

ከዚህ ጊዜ ወዲህ ክርስቲያኖች ዕረፍትና ሰላም በአገኙበት ዘመን እንደ ዠመ ሩት ባንድ ስም በኅብረት ያረመኔውን አገር ሁሉ አስተምረው በክርስቶስ አላም ነው ሳይጨርሱ ወደፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ከመካከላቸው አንዳንድ የተመረመ ርሁ ሊቅ ነኝ የሚል እየተነሣ እርስ በርሳቸው መለያየትና መጣላት ዠመሩ ።

፩ኛ. ከሁሉ በፊት ዓይነተኛ ጠብ የዠመረው ያ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በዚሁ ጠብ ምክንያት ስመጥር የሆነው (ARIUS) አርዮስ ነው ። እር ዮስ በፊት የባውካሊስ (ሊቢያ) ካህን የነበረ ነው ። በኋላ ወደ እስክንድርያ መጥቶ ተቀመጠ ። እርሱም «ክርስቶስ ቃል ወይም ልጅ ስለሆነ የተገኘበት (የተወለደበት) ዘመን ስላለው ከዘለዓለማዊው ከአብ ጋር ትክክለኛነት (ዕሪና) የለውም ። ጠባዩም (HOMOUSSIOS) የክርስቶስ ከአብ ያለ ያልና ምንም አዳኛችን ቢሆን ከአብ ጋር እኩል አምላክ ልንለው አይገባም የሚል ትምህርት አመጣ ። በዘመኑ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አባ እለ እስክንድሮስ እንደዚህ የመሰለውን ትምህርት እንዲተው ቢገ ዝተው እምቢ አለው ። ትምህርቱንም እያደረ በያለበት ማስፋፋት ዠመረ ።

(፩) ወይዘን ሊቀ እምኔሆሙ ወመኩንን በዓለ መንበረ ጴጥሮስ ዘሮምያ በከመ አዘዙ ሐዋርያት ። ወ ምድኅሬሁ በዓለ እስክንድርያ ዓባይ ወውእቱ መንበረ ማርቆስ ። ወካልእ በዓለ ኤፌሶን . . . ወሬ ብእ በዓለ መንበረ አንጾኪያ . . . . ፍትሐ ነገሥት አራተኛው አንቀጽ

ስለዚህ እ. አው. ቀ. በ፫፻፳፭ ዓ.ም. ትልቁ ቆስጠንጢኖስ በተቀመጠበት ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉዳዩን መርምረው ለመወሰን ከያለበት ተሰበሰቡ ። ከሳሽ (አፈ ጉባኤ) ሆኖ የቆመው እለእስክንድሮስና ተከታዩ አትናቴዎስ ባንድ ወገን ተከሳሹ አርዮስ በሌላው ወገን ሆነው በነዚህ ሊቃውንት ፊት ተከራከረው አርዮስ ተረታና ተወገዘ ። የተሰበሰቡትም ሊቃውንት ክርስቲያን ሁሉ እንዲ ያምንበት ጸሎተ ሃይማኖት የሚባለውን አዘጋጅተው ያን ጊዜ የሰጡት እነሆ እስከዛሬ ድረስ ለጸሎት እንጠቀምበለታን ። የረችዎቹ ጥቅስ «እኔና አብ አንድ ነን» ተብሎ በዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው «ሂዱና በአብ በወልድ በመ ንፈስ ቅዱስ ስም አሕዛብን አጥምቁ» ተብሎ በማቴዎስ ወንጌል የተጻፈውና እንደዚሁም ይኸን የመሳሰለው ነው (1) ።

፪ኛ. መቅዶንዮስ (Macedonius) የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በቫለንትያኖስና በወ ንድሙ በቫሌንቱስ ዘመን ፫፻፷፬ - ፫፻፸፬ (፫፻፶፯ - ፫፻፷፪) ዓ. ም. ዘሠረፀ እም አብ (መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣ) የሚለውን ተከትሎ ከሦስቱ አካላት ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የወጣ (የተፈ ጠረ) ስለሆነ ከሁለቱ አካላት ከአብና ከወልድ ያንሣል (መንፈስ ቅዱስ ሕጸጽ) ስላለ በዚሁ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከአባ ጢሞቴዎስ ጋር በቊስ ጥንጥንያ ክርክር ሆኖ መቅዶንዮስ ተረቺ ጢሞቴዎስ ረቺ ተብለው ተለያዩ።

፫ኛ. ንስጥሮስ (NESTORIUS) የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት እንደ አው. ቀ. [SIC] በ፬፻፴፩ ዓ. ም. ላይ ለክርስቶስ መለኮታ ዊና ሰውነታዊ ሁለት ባሕርያት ፣ የመለኮትና የሰውነት ሁለት አካላት ስለ አሉት በመለኮቱ ማርያም አልወለደችውምና ወላዲተ አምላክ (Theotokos) ልትባል አይገባም ። ክርስቶስም በሰውነቱ ከአብ አይወለድምና የጸጋ ልጅ ስለሆነ የክርስቶስ እናት ( CHRISTOTOCOS ) ትባል የሚል አሳብ ስላመጣ ይኸማ ሁለት ልጅ አራት አማልክት ማድረግህ ነው ተብሎ በ፬፻፴፩ ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ ሆኖ የሮማው ሊቀ ጳጳስ አባ ሴሌስተ ፩ኛ (2) የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ቄርሎስ ባንድነት ሆነው ተከራከረው ቄር ሎስ ረታ ንስጥሮስ ተረታ ተብሎ ንስጥሮስ በግዞት ወደ እስያ ሄዶ ቄርሎስም በደስታ ወደ ሥፍራው ወደ እስክንድርያ ተመለሰ ።

፬ኛ. አውጣኪስ (AUTICHES) የሚባል የግሪክ መነኵሴ ያንድ ባሕርይን እም ነት ይዞ የንስጥሮሳውያንንም እምነት እየተቃወመ ኖሮ ራሱ ደግሞ ለክርስ ቶስ ከሰው የተለየ ረቂቅ አካል አለው ። አካሉም እንደ ሰው ሥጋ አይታመ

(1) የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 10 የማቴ. ወንጌል ምዕ. 28 ።

(2) በገድለ ፋሲለደስ ውስጥ የዚህ ሊቀ ጳጳስ ስሙ በግዕዝ አቡነ ቅዱስ ከለስቲኖስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀ ገረ ዓባይ ሮሜ ተብሎ ይገኛል ። የቺሊያም ራይትን ካታሎግ ገጽ 186 ቍጥር CCLXXII ተመልከት ።

ምም የሚል አሳብ ስላመጣ በዚሁ ፍላቭያኖስ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በ፬፻፵፰ (፬፻፵) ዓ. ም. ተከራክሮ ረቂቅ ሥጋ እንዳይል ገዘተው ።

፳፯. ፍላቭያኖስ (FLAVIANUS) ራሱ ለክርስቶስ መለኮታዊና ሥጋዊ ፪ ባሕርያት አሉት ማለትን ስለአጸና በዚሁ የተነሣ የቄርሎስ ተከታይ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ዲዮስቆሮስ (DIOSCORUS) ለክርስቶስ መለኮቱና ሰውነቱ የተዋሐደ አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት ባሕርያት የሉትም ስላለ በዚህ ክርክር ገጥመው ክርክሩም እያደር ወደ ጠብ ደርሶ ወገን ለወገን እየተለያዩ እስከ መደባደብ ደርሰዋል ። ይሁን እንጂ እንደተለመደ ክርክሩ በሊቃውንት ጉባኤ ይታይ ተባለና በዚሁ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመን በ፬፻፵፩ (፬፻፵፱) ዓ. ም. በኤፌሶን (ግሪክ) ስብሰባ ተደረገ ። በጉባኤው ላይ ብዙ ክርክር ሆኖ መጨረሻውን የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ዲዮስቆሮስ ረታ የቁስጥንያው ሊቀ ጳጳስ አባ ፍልቭያኖስ ተረታ ተብሎ የክርክሩ ፍጻሜ ሆኖ ጉባኤው በተበተነ በ፫ኛው ቀን ፍላቭያኖስ ሞተ ። የሞተውም የዲዮስቆሮስ ወገኖች (እንደ ግማሾቹም ራሱ ዲዎስቆሮስ ጭምር) በደበደቡት ሕመም ነው ተባለ ።

ከዚህ ከኤፌሶን ጉባኤ በኋላ ድል አድርጎ ዲዮስቆሮስ በደስታ ወደ ሥልጣኑ ሥፍራ ወደ እስክንድርያ ተመለሰ ። ዳሩ ግን በምዕራብ በሮማ ፤ በምሥራቅ በቍስጥንጥንያ (ትንሹ ሮማ) ግዛት ለክርስቶስ የሰውነትና የመለኮትነት ሁለት ባሕርያት አሉት ሰውነቱ ይበላ ይጠጣ ያዝን ያለቅስ ነበር ፤ በመለኮቱ ግን ዓይን አበራ ሙታን አሥነሣ እያሉ የሚያምኑት ወገኖች እየበረከቱ ሄዱ ። የዲዮስቆሮስ ወገኖች የክርስቶስ ሰውነታዊ ባሕርዩና መለኮትነቱ አንድ ሆኖ ተዋሕዷልና የክርስቶስ ባሕርይ አንድ እንጂ ሁለት ሊባል አይችልም የሚሉት በኤፌሶን ጉባኤ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ጊዜ አሸናፊ የነበሩት ቍጥራቸው ያንስ ዠመር ። ቢሆንም በእስክንድርያና በታናሿ እስያም በሶርያ በአንጾኪያ ብዙዎቹ ይኸንኑ ያንድ ባሕርይን (MONOPHYSISME) እምነት አጽንተው ስለያዙ የሁለት ባሕርይ ወገኖች እንደልባቸው ሊስፋፉ አልቻሉም ።

ዳሩ ግን ቀድሞ ያንድ ባሕርይ ወገኖች በዲዮስቆሮስ መሪነት አሸናፊ የሆኑት ንጉሡ ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ራሱ የዚህኑ ያንድ ባሕርይን እምነት ስለያዘና በየጉባኤው እየተገኘ ስለደገፈው ነበር ። አሁን ግን እርሱ ሞቶ ከርሱ ቀጥሎ የነገሠው መርቅያን (MARKIANUS) ና ሚስቱ ብርክልያ (PULCHERIA) የሁለት ባሕርይን አሳብ ስለደገፉ መርቅያን በነገሠበት ጊዜ እንደገና በጉባኤ ይታይ የሚል ትእዛዝ በያለበት ታዘዘ ። በዚሁ መሠረት የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ዲዮስቆሮስ እንደገና ከእስክንድርያ ወገኖቹን ይዞ ወደ ቍስጥንጥንያ ሄደ ። ከዚያም ሊቃውንት ከያለበት ተጠራቅመው በጉባኤ እንዲታይ ወደተወሰነበት ከተማ ወደ ኬልቄዶን (Chalcedoine) በ፬፻፵፫ (፬፻፶፩) ዓ. ም. ሁሉም ተሰበሰቡ ። ቍጥራቸው በድምሩ የሊቃነ ጳጳሳቱም የኤጲስ ቆጶሳቱም የሊቃውንቱም ፮፻፴ ይደርሳል ይባላል ። ጉባኤው ከተከፈተ በኋላ ሁለቱም ወገኖች በጥቅስና በሙግት ስለበረቱ ሁለ

ቱም ወገኖች ደጋፊ ስላገኙ ረቺውንና ተረቺውን መለየት አቃተ ።

ስለዚህ በመጨረሻ በጉባኤው የሁሉም አለቃ ከመሆኑ የተነሣ ሳይመጣ የቀረው የሮማው ሊቀ ጳጳስ ልዮን ይመስክር ብለው በርሱ ምስክርነት ተዋደዱ ። የርሱ ምስክርነት ከሮማ እስኪመጣ ድረስ ሁለቱ ባላጋራዎች በነገር ክርክር ሲዋለቁ ሰንብተው የልዮን ምስክርነት ከመጣ በኋላ ለመስማት እንደገና ተሰበሰቡ ። በጉባኤው ላይ ከሮማ የመጣው የልዮን ደብዳቤ ሲነበብ ለክርስቶስ ሰውነታዊና መለኮታዊ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚል ሆነ ። በዚህ ጊዜ በዚያ ያሉት ጳጳሳትና ሊቃውንት ዲዮስቆሮስን ሁለት ባሕርይን ተቀበል እምቢ ታልህ ገዝተንሃል አሉት እርሱም ሁለት ባሕርይ ማለትን አልቀበልም ። እናንተም እንዳትሉ ሲል በዚያ ያሉትን ጳጳሳትና የሌለውን የሮማውን ሊቀ ጳጳስ ልዮንን መልሶ ገዘታቸው ። ያን ጊዜ በጉባኤው ታላቅ ሁከትና ጭቅጭቅ ሆነ ። ከዚህ በኋላ ለሁለት ባሕርይ ወገኖች ቀናተኛ በሆነችው በብርክልያ (የንጉሡ ሚስት) ትእዛዝ ዲዮስቆሮስ ተያዘና ጥርሱ እስኪሰበር ድረስ እየደበደቡ የከበረውን ጢሙን ላጭተው ወደ ካንግራ ደሴት (ገላትያ የዛሬ ቱርክ) ወስደው እንዳሠሩት በ፫ኛው ዓመት ሞተ ።

ይሁን እንጂ አባ እለእስክንድሮስ ፤ አባ አትናቴዎስ ፤ አባ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ አባ ቄርሎስ አውጣኪስ የተጋደሉበት ያንድ ባሕርይ እምነት በታናሽ እስያና በሮማ ኃይሉ ቢቀነስም ፤ ቢቀዘቅዝም በዋናው መደበኛ ሥፍራው በእስክንድርያ በኢትዮጵያ (በአክሱም)ና በኖብያ (ሱዳን) ጸንቷ131Cሯ ። ባንዳንድ ጥቃቅን አባብና ሥርዓት ቢለያይም ከሁለቱ ባሕርይና ከንስጥሮሳውያን ከአርዮሳውያን እየተከላከለ በታናሽ እስያ እንደዚሁም በመስኮብና በአርመን ጸድቆ ይኖራል ። ቀጥሎም ባለው ጊዜ ውስጥ ፭፻፳፯ · ፭፻፷፭ (፭፻፳ - ፭፻፵፰) ዮስጥንያኖስ (JUSTINIANUS) ቢነግሥና እርሱም የሮማን ሊቀ ጳጳስ የልዮንን ሁለት ባሕርይን ቢከተል የታወቀችውና ኃይለኛዪቱ ሚስቱ ታኦድራ (THEODORA) ያንድ ባሕርይን እምነት ስለደገፈች እንደገና ተዋሕዶዎች አንሠራሩ (1) ።

መቼም የዚያን ዘመን ሊቃውንት ስለመለኮትና ስለ ሰውነት ስለ ባሕርይ ያላቸው ምርምር ዓይነቱ ብዛቱ ርቀቱ ጥልቀቱ ስፋቱ ብዙ ስለሆነ በዚህ ባንድና በሁለት ምዕራፍ የሚወሰን አይደለም ። ነገርግን ኢትዮጵያውያንን በአሁኑ ሰዓት ሊረዱ ሊዛመዱ ከመጡት የፖርቱጋሎች ጋር ለዝምድናው እንቅፋት የሆነው ይህ ያንድ ባሕርይና የሁለት ባሕርይ እምነት ስለሆነ ሁኔታውን የዛሬ ወጣት ባጭሩ እንዲረዳው ትንሽ ለማብራራት እሞክራለሁ ።

እላይ እንዳነበብነው በ፬፻፴፩ ዓ. ም. በንጉሡ ነገሥት ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ሰብሳቢነት በኤፌሶን ጉባኤ ላይ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ለክርስቶስ ሁለት የአምላክና የሰውነት አካላት ሁለት የአምላክና የሰውነት ባሕርያት አሉት ባለ ጊዜ

(1) Les Conciles oecumenique dans l'histoire - salles-DABADIE ገጽ 15 - 123 ሃይማኖተ አበውንና መዝገበ ሃይማኖት የሚባለውን በየሥፍራው ። Scriti TEOLOGIE etiopici በሚል አርእስት ቸሩሊ ያሳተመውን ገጽ 3 - 34 ተመልከት ።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቄርሎስ የለም ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋዊና መለኮታዊ ባሕርዩ ባንድ አካል ላይ ነው ያለው ብሎ መልስ በመስጠት ረትቶ የተለያዩትን እንደገና የንስጥሮስ ተከታይ ፍላቭያኖስ አሳቡን በአጋማሽ ከንስጥሮስ ለየት አድርጎ ክርስቶስ ፩ አካል ነገር ግን አንዱ የክርስቶስ አካል ሁለት የሰውነትና የመለኮትነት ይኸም ማለት የአምላክነት ባሕርይ አለው ሲል የሮማው ሊቀ ጳጳስ ይኸንኑ አጽድቆ አብራርቶ የኬልቄዶኑ ጉባኤ ይኸንኑ በይፋ እንዲያጸድቅ አደረገ ። ለዚህም ማብራሪያ ሲሰጥ ሁለቱ ባሕርያት የየግል ተግባራቸውን ይፈጽማሉ ይኸውም ማለት ሰውነት የሰውነትን መለኮት የመለኮትነትን ይሠራል ። ሰውነቱ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ አለቀሰ ፤ ይኸን ሞት አስወግድልኝ ብሎ ወደ አባቱ ጸለየ (1) ። በመለኮቱ ዕውር አበራ ፤ ለምፃምን ፈወሰ ፤ የሞተውን አሥነሣ ። እርሱ ራሱ ከሞተ በኋላ ተነሣ (2) ።

ስለዚህ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ከዚሁ ተያይዞ ሁለት ፈቃድ ሁለት ሥምረት አለው አሉ (3) ።

ተዋሕዶዎቹ ለዚህ መልስ ሲሰጡ ይኸማ አልሸሸም ዞወር አሉ እንደሚባለው ምንም እንኳን ፩ አካል ብትሉ ሁለት ባሕርያት ከአላችሁ ከዚያው ከተወገዘው ከንስጥሮስ አልራቃችሁም ። የተዋሕዶ ባሕርዩን ከሁለት ከከፈላችሁት የተሰቀለው የሞተውና በሞቱ ያዳነን የትኛው ነው ። በቃና ዘገሊላ ሠርግ ገብቶ ወይኑን ውኃ ማድረግ የቻለው ዓይነተኛው ነው ። ሰውነቱ ነው ያላችሁ እንደሆነ የሰው ሥጋና ሕይወት ሞቶ ሰውን ከሲኦል ሊያድን አይችልም ፤ ከዚህ በፊት የሞቱት የነአብርሃምና የነሙሴ ሞት ማንንም አላዳነም ።

በዚህ ምክንያት ክርስቶስ አምላካዊና ሰውነታዊ ባሕርዩ በፍጹም ተዋሕዶ አንድ በመሆን ፩ አካል አንድ ባሕርይ አንድ ፈቃድ ነው ያለው ። እንደናንተ ሁለት ባሕርይ ሁለት ፈቃድ አንዱ የሚታመም አንዱ የማይታመም አንዱ ባሕርይ የሚያድን አንዱ የማያድን ሁለት ነው ስትሉ የቄርሎስን ፩ ባሕርይ እምነት እጥፍታችሁ እንዱ ክርስቶስ ሁለት ሆኖ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አራት ሆኖ እንደ ንስጥሮስ አራት አምላክ ልታደርጉት ነውና አይሆንም አሉ (4) ።

እንግዲህ የሁለቱ ወገኖች ክርክር ዋናው ፍሬ ነገር እዚህ ላይ ይቆማል ። በዚሁ መሠረት ግን ጥቅስ ከየአለበት እየተጠቀሰ ዝርዝሩ ሐተታ ብዙ ነው ። እንደዚሁም በዚያ የሃይማኖት ክርክር በቁም ነገር በሚታይበት ዘመን ተዋሕዶዎቹ ከሌሎች አማናውያን ጋር የሚለያዩበት ብዙ ስለሆነ ብዙውን ዝርዝሩን በዚህ ምዕራፍ ለማዳረስ አይቻልም ።

(1) የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 11 ቍ. 34 - 35 ፤ ማቴ. ምዕ. 38 ቍ. 38 - 41

(2) ማቴ. ምዕ. 9 ምዕ. 25

(3) የፈረንሳዩ essence ያለውን የኛዎቹ ስምረት ብለውታል (ሁናቴ አፈጣጠር ?)

(4) መጽሐፈ ልቡና ቼሩሊ ፲፱፻፰ ዓ. ም. ያሳተመው ገጽ 10 - 14 ፤ 155 - 160

## ምዕራፍ ፻፴፫
## በክርስትና እምነት የኢትዮጵያ ጉራ - የ፩ ባሕርዮችና የ፪ ባሕርዮች የቆየ ጠብና ክርክር

እንግዲህ በሊቃነ ጳጳሳት ማዕርግ ፭ኛ በጴጥሮስ መንበር የሚቀመጠው የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ሲሆን ከርሱ የሚከተለው ከሌሎቹ የሚበልጠው የእስክንድርያው መሆኑን ከአነበብን ወዲህ በኬልቄዶን ጠብ ምክንያት የሮማና የእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ፈጽመው ተለያዩ ። በሮማ የሊቃነ ጳጳሳቱ ሥልጣን በካቶሊኮቹ የአውሮፓ ነገሥታት ምክንያት ከፍ ያለ በዓለም ተከታዩም የበረከተ ቢሆንም በበኩሏ እስክንድርያም በማርቆስ መንበር የሚከታተሉት የፓትሪያርኮች መቀመጫ የሊቃውንትና የቀለም ሰዎች መሰብሰቢያና መገኛ በጠቅላላው ከሮማ ቀጥሎ የዘመናዊው የመንፈሳዊና የሥጋዊ ዕውቀት መደብ ሆነች ። ከሮማ ሁለተኛዋ የሆነችው ከክርስትና ዘመናት ወዲህ ባለው ድርጅት በርሷ እያደር መቀዝቀዝ በሮማ እያደር ማደግ የተነሣ ነው እንጂ ከክርስትና በፊት የዕውቀት መደብር በመሆን እስክንድርያ ከሮማ ብትበልጥ እንጂ አታንስም ነበር ።

የአክሱም መንግሥት በገነነበት ዘመን በአራተኛው መቶ ዓ.ም. ላይ በአብርሃና በአጽብሐ ጊዜ አባ ሰላማ የተባሉት ፍሬምናጦስ ክርስትናን ከእስክንድርያ ወርሰው በኢትዮጵያ አስገቡ ። የዚህ ታሪክ በየመጽሐፉ ስለተጻፈ እዚህ ላይ መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም (1) ። ይህ የክርስትና ሃይማኖት እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ "፭ኛ መቶ ዓ. ም." አንድ ባሕርይ ሁለት ባሕርይ የሚባለው ጠብ ገና ስለአልተቀሰቀሰ እንደዚሁ የክርስትናው ሃይማኖት ሐዋርያትና የኒቅያ ጉባኤ ያስተማሩት ቀጥተኛው ትምህርት ብቻ በኢትዮጵያ ተስፋፋ ። እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ የእስክንድርያ ፓትሪያርኮች በሮማ ፤ የሮማ ሊቃነ ጳጳሳት በእስክንድርያ በዚያው በየደረጃቸው ሲከባበሩ ልዮን አንደኛ ወይም ትልቁ "፬፻፶-፬፻፶፩ ዓ.ም." በሮማ ፤ ዲዮስቆሮስ በእስክንድርያ ፤ ፍላቭያኖስ በቍስጥንጥንያ እስከ ተሾመበት ጊዜ ደረሱ ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ በጠቅላላው እየተባበሩ ባለፈው ምዕራፍ የተመለከትነውን የአርዮስን ፤ የመቅዶንዮስን ፤ የንስጥሮስን አንሣሥ አወገዙ ። አውጣኪስ የሚባለው እንኳን የግሪክ መነኵሴና ሊቅ በክርስቶስ አንድ ባሕርይነት ከዲዮስቆሮስ ሲስማማ ለክርስቶስ ረቂቅ ሥጋ በሰጠበት የተነሣ ሁለቱም ወገኖች ያወገዙት ባንድነት ነው ።

ነገር ግን በሁለቱ ወገኖች መካከል የመጀመሪያው ጠብ በኤፌሶን ጉባኤ ከተወጠነ በኋላ አንደኛውን በኬልቄዶን ጉባኤ ጕልቶ መመሥረት ቻለ ። በዚያን ዘመን ታላላቅ ከተሞች በሆኑት በእስክንድርያ በቍስጥንጥንያ በአንጾኪያ በኤፌሶን ሊቃነ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሌሎችም ደረጃም ባይኖራቸው የክርስቲያን መምህራንና ተማሪ መጻሕፍት መርማሪ በያለበት በረከተ ። የትምህርቱም ዋናው መሠ

(1) የኢትዮጵያ ታሪክ — ኑብያ ፡ አክሱም ፡ ዛጕዌ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ ምዕራፍ 49 ፡ 50

ረት ብሉይና ሐዲስ ቢሆንም በዚያ ውስጥ ግን በቅርብ ከማርያም ሥጋ ለብሶ የተወለደው አምላክ ሥጋው ባሕርዩ ከሦስቱ አካላት "ሥላሴ" ጋር ያለው ግንኙነት እንደምን ነው ? ። ወንጌላዊው ዮሐንስ ቃል አስቀድሞ ነበር ቃል ሥጋ ሆነ የሚለው እንዴት ነው ? የሚሉ ጥልቅ ምርምር በርክቶ ነበር ።

ዋናው ጠቅላላ እምነት በኒቅያ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ ባለበት ቢወሰንም የዘለቄታ ውሳኔ ሆኖ በሚቀጥለው ጊዜ ሰላም አልተገኘም ። ስለዚህ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፤ ፍላቭያኖስ ለክርስቶስ መለኮታዊና ሥጋዊ ሁለት የተለያዩ ባሕርያት አሉት ብሎ ባነሣው ጠብ በነገሥታቱ በነዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ርዳታ ጭምር በኤፌሶን መረታቱ ላንድ ባሕርዮች ደስታ ሲሰጥ ለሁለት ባሕርዮች ኀዘንን አተረፈ ። በሚቀጥለው በኬልቄዶኑ ጉባኤ ደግሞ በቴዎዶስዮስ ተከታይ በማርኪያኑስና በሚስቱ በቡልኼሪያ ድጋፍ አንድ ባሕርዮች ተረቱ ተብሎ በዚሁ ዋናው ተከራካሪ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ዲዮስቆሮስ ተደብድቦ ሲታሠር ባንድ ባሕርዮች ዘንድ የነበረው ደስታ ወደ ኀዘን ተለወጠ ።

በዚህ ዘመን ባለው የሃይማኖት ክርክር ነገሥታቱ በየዋናው ጉባኤ በተሰበሰቡት ጳጳሳት መካከል እየተቀመጡ መዳኘት ስለአለባቸው በኒቅያ ጉባኤ ጊዜ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ እንደነበረ አሁንም በኤፌሶኑ ጉባኤ ቴዎዶስዮስ ትልቁ በኬልቄዶኑ ማርኪያኑስ ተገኝተው ልባቸውና ጉባኤው ላደላው ወገን እየሆኑ በተረቺው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ይፈጽማሉ ። እነዚህም ነገሥታት የቍስጥንጥንያ ነገሥታት ናቸው ። ቍስጥንጥንያ ማለትም ዛሬ የቱርክ ከተማ የሆነው ስጣንቡል ነው ። ቄሣሮቹ በዚህ ከተማ ሆነው የምሥራቅ የቄሣር ግዛት የሚባለውን የዛሬዎቹን የባልካን አገሮች የመካከለኛው ምሥራቅንና ግብፅን ጨምሮ እየገዛ በበላይ የሚያስተዳድር ነው ።

በኤፌሶን የአንድ ባሕርዮች ድል ማድረግ ቀድሞውኑ የሮማን ቤተ ክርስቲያን አላስደሰተም ነበር ። በኤፌሶን ጉባኤ ተረቱ እየተባሉ የታሠሩት ሁሉ እየተፋቱ አንድ ባሕርዮች በኤፌሶን የዚህ ጉዳይ አልቋልና እንደገና መታየት የለበትም እያሉ ሲከራከሩ የሮማው ሊቀ ጳጳስ ልዮንና የቍስጥንጥንያው ንጉሥ ማርኪያኑስ በመተባበር በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ አንድ ባሕርዮችን ስለ አስረቱ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ (1) በሮማ ቤተ ክርስቲያንና በእስክንድርያ መካከል ያለው ግንኙነት ፈጽሞ ተበላሽቶ ተለያዩ ።

ክርስቲያኒቱ ኢትዮጵያ የምትከተለው ክርስትናን የተቀበለችበትን ክህነት ቅስና የሚሰጠውን ቀብቶ የሚያነግሠውን ጳጳስ የምታገኝበትን የእስክንድርያን የመንበረ ማርቆስን ስለሆነ በርሷም ዘንድ የሮማ ቤተ ክርስቲያን የተጠላ ሆነ ።

ከአምስተኛው መቶ ዓ. ም. ዠምሮ ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ በሰፊው በቍስጥንጥንያ ግዛት የነበሩት ያንድ ባሕርይ አማኞች በየመልኩና በየጊዜው ብዙ መጉላላትና መጕጠጥ ስለደረሰባቸው ሁለት ባሕርይ የሚሉትን በሥልጣን ላይ ያሉትን

(1) እ. አው. ቍ. 453 ዓ. ም.

ጠላቶቻቸውን በመሸሽ ከቊስጥንጥንያ ከአንጾኪያ ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ባንድ ባሕርይ መሠረት የክርስትናን ትምህርት አስፋፉ ። ከነዚህም መካከል ዛሬ ገዳም ተሠርቶላቸው ታቦት ተቀርጾላቸው ቅዱሳን ጻድቃን እየተባሉ የሚጠሩት የሺምዛናው አባ መጣዕ ፤ ዘጠኙ ቅዱሳን የሚባሉት የደብረ ዳሞው አባ ሚካኤል "አቡነ አረጋዊ" የዓድዋው አባ ገሪማ የዩሐው አባ አፍጼ ናቸው የቀሩትም እንደ ዚሁ በየአውራጃው ክርስትናን አስፋፉ ።

ቀጥሎ ባለው ጊዜ የነርሱን መሪ ትምህርት በመከተል ከአገር ተወላጅ ውስጥ እንደነ አባ ዮሐኒ ፤ እንደነ አባ ኢየሱስ ሞዓ ፤ እንደነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤ እንደነ እጨጌ ፊልጶስ ያሉ ከፍተኛ የቤተ ክህነት አባቶች በየጊዜው ከየአውራጃው እየተነሡ ከግብፅ ከሚመጡት ጳጳሳት በዙፋን ከሚወጡት ነገሥታት ጋር በመተባበር ይህን የተዋሕዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘንድ አጸኑት ። ይኸም እስከዚህ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግልና እስከ ዓፄ ገላውዴዎስ የደረሰው ዛሬም የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሃይማኖት የሆነው የተዋሕዶ ሃይማኖት ነው ።

በዚህም ጊዜ ብዙ መንፈሳዊ መጻሕፍት በተለይ አንድ ባሕርይን የሚደግፉ እነዚያን ሁለት ባሕርይ የሚሉትን የሚጸርፉ ከኮፕት ፤ ከግሪክ ፤ ከሶርያ ፤ ከዓረብ ወደ ግዕዝ እየተተረጐሙ ተበተኑ ። የተተረጐሙትንም ሊቃውንት ካህናት መነኰሳት እጨጌዎች የገዳም አበው ሁሉ እያነበቡ በየጊዜው በያገሩ በየገዳሙ አስፋፉት ። እነዚህ መጻሕፍት ይበልጥ ወደ ግዕዝ[illegible]ተረጐሙ ባገራችን የተስፋፉበት ጊዜ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን ፲፫፻፯ - ፲፫፻፴፯ ዓ. ም." ገምሮ ነው ። በነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ በነዓፄ ናዖድ በዚህም ባፄ ልብነ ድንግልና ባፄ ገላውዴዎስ ዘመን በብዛት ተተርጕመው የሃይማኖታችንና የሥነ ጽሑፋችን መሠረት ሆነዋል ። ራሱ ስለ ሃይማኖት አስፋፍቶ የሚናገረው ሃይማኖተ አበው የሚባለው መጽሐፍ መብዓ ጽዮን የሚባለው የራስ ዓምዱ ልጅ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጐመው በኻሁ በወጣት ንጉሠ ነገሥት ባፄ ገላውዴዎስ ዘመን ነው ።

እንግዲህ ከአብርሃ ወአጽብሐ ገምሮ በዛጕዬዎች በኵል አልፎ ከነዚሀ ከአማራዎቹ ነገሥታት ዘመን ደርሶ እስከ ጊዜያችን መዝለቅ የቻለው የክርስትና ሃይማኖት ፈረንጆች (MONOPHISISME) አንድ ባሕርይ የሚሉት የተዋሕዶ ሃይማኖት በመካከለኛው ምሥራቅ በያለበት የተበታተኑ ቢኖሩም በተለይ ለዚህ እምነት የግብፅ የኢትዮጵያ የኖብያ (1) አብያተ ክርስቲያናት ተባብረው አንድ ጕራ ፈጥረው የዲዮስቆሮስን ጠላቶች ሁለት ባሕርይ የሚሉትን ሁሉ ይጠሉ ገመር ።

የጉባኤው የአንደበቱ ክርክር አንዳንድ ጊዜ ወደ መደባደብ ስለሚለወጥ በኤፌሶን ጉባኤ ዲዮስቆሮስና ወገኖቹ ፍላቭያኖስንና ወገኖቹን ደብድበው እንደነበረው በኬልቄዶኑ ጉባኤ ጊዜ ከሮማው ጳጳስ ምስክርነት ወዲህ ሁለት ባሕርዮች በንጉሠ ነገሥቱ በመርቅያንና በሚስቱ እየተደገፉ ሥልጣኑ ካንተ በላይ የሆነው የሮማው ሊቀ ጳጳስ ልዮን ሲመሰክርብህ ተቀበል ብለውት ዲዮስቆሮስ የርሱ በላይ

(1) የዛሬው ሱዳን ከዓረብ ወረራ በፊት

ነት በቀናችዩ-ቱ የሃይማኖት መሥመር እስከተራመደ ድረስ ነው እሁን ግን አባ ቄር ሎስም ሁላችንም የምናምናትን በኤፌሶን ጉባኤ የጸደቀችውን ተዋሕዶ ሃይማኖት ከለወጠ ከሐዲ ነው እንጂ የበላያችን አይደለምና ገዝቼዋለሁ ብሎ የምስክርነቱ ንም ደብዳቤ (1) በአደባባይ ስለቀደደው ደብድበው ይኸም አልበቃ ብሎ ጥርሱን ሰብረው ጢሙን ላጭተው በደሴተ ጋግራ አሥረውት በዚሁ ስለሞተ ይኸ የኬልቄ ዶን ጉባኤ ከነቀሳውስቱ ከንጉሡና ከሚስቱ ከመስካሪው ከልዮን ጋር በሙሉ በተ ዋሕዶዎች ዘንድ የተጠላ የተረገመ ነው ።

የፊተኛውን የኤፌሶኑን ጉባኤ ካቶሊኮቹና ሁለት ባሕርዮች "የወንበዴዎች ጉባኤ" ይሉት እንደነበረ በተዋሕዶዎች ዘንድ የኬልቄዶኑ ጉባኤ "ማኅበረ ከለ ባት - የውሾች ጉባኤ" ተብሎ ተሠየመ ። ምስክርነቱን በደብዳቤ የሰጠው ልዮን "መሣጢ ርኩስ" ወይም "ልዮን ስሕተተኛው የክህደትና የወንጀል መዝገብ ማደ ሪያ ወይም ከረጢት" ተባለ (2) ። በዚያ የነበሩት ጉባኤውን ተካፍለው ዲዮስቆሮ ስን የተቃወሙት ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት "የስንፍና መምህራን ሃይማኖትን የሚ ያፈርሱ" (3) ። በንጉሡ ነገሥትነት ጉባኤውን የመራው ማርኪያኑስ "መርቅያን" ሚስቱ ቡርኬሌ "ብርክልያ" "ንስጥሮሳውያን" እየተባሉ የስድብ ስያሜ ተሰጣ ቸው ።

ድርሳነ ማርያም የሚባለው መጽሐፍ የቅዱስ ዲዮስቆሮስ እሟሟት ብርክል ያን ያለ ዘር አስቀራት መቅፅንንም ከዕድሜው በፊት ቀሰፈው ተከታዮቹም ተኰ ነኑ ልዮንም ጠፉ ለማለት በግዕዝኛ ቋንቋው እንደዚህ ይላል «ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘተጻብዓ በአሠሮሙ ለሐዋርያት በቅድመ ጉባኤ ዓላዊ ኬልቄዶናዊ ርኩስ ፤ ወዘአ ስተርከበት ጸሎቱ ሞተ ላዕለ መርቅያን እምቅድመ መዋዕሊሁ ፤ ወኀደጋ ለብርከ ልያ ንግሥት ዘእንበለ ፍሬ ወሠረፃ ለልዮናልዮስ ውስተ ዕመቀ ገሀነም ፤ ወለዮስ ትንያኖስኒ ፈነዎ ኀበ ማዕምቅ ፤ ወአጥፍአ ለልዮን» (4) ።

በነርሱ አንጻር የሚገኙት ስለ አንድ ባሕርይ ሲሟገቱ ሲታገሉ ሲታሠሩ የኖ ሩት ወይም ከመከፋፈል በፊት የነበሩት የእስክንድርያውና የቊስጥንጥንያው ሊቃነ ጳጳሳትና ከነርሱ በፊት የነበሩት መምህራን አበው በነዚያ ስድብ መጠን ለነ ዚሀ የተዘጋጀው የቅጽል ስም የሚያወድስ መሆኑን በሚከተለው እንመልከት ።

ሀ. አትናቴዎስ የሕይወት ምንጭ "ነቅዓ ማየ ሕይወት" (5)

ለ. ባስልዮስ የሃይማኖት መብራት "ማኅቶተ ሃይማኖት" (6)

(1) ግዕዙ ጦማረ ልዮን እብድ ይለዋል ።
(2) ልዮን ስሑት መዝገበ ዕልወት ወአመጻ
(3) መምህራነ ዕበድ ነሣትያነ ሃይማኖት
(4) ልዮናልዮስ የሚለው የቢዛንቱ ሊዎንስ የሚባለውን የ፪ ባሕርይ ሊቅ የዩስጥንያኖስን መምህር ነው ፤ ዮስጥንያኖስ የንግሥት ቴዎዶራ ባለቤት ሁለት ባሕርዮችን የደገፈ ንጉሠ ነገሥት ነው ፤
(5) የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ፍሬምናጦስን ለጵጵስና ቀብተው ወደ ኢትዮጵያ የላኩ ፤
(6) ሁለት ባስልዮስ አንዱ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ አንደኛው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ ተመስጋኙ የቂሣርያው ኤጲስ ቆጶስ ነው ።

ሐ. ጎርጎርዮስ የመለኮትን ምሥጢር አዋቂ "ነባቢ መለኮት እንዳንድ ጊዜም ገባሬ ተአምራት ይባላል ። (1)

መ. አፈ ወርቅ የዕውቀት ከረጢት "መዝገበ ልቡና" (2)

ሠ. ቄርሎስ የሃይማኖት ምሰሶ "ዓምደ ሃይማኖት" (3)

ራሱ ስለ አንድ ባሕርይ የሞተው ዲዮስቆሮስ የበለጠ በወገኖቹ ዘንድ የተሞገሰና የተወደሰ ነው ። እነዚህ ሁሉ የሃይማኖት አባቶች በግብፅና በኖብያ በኢትዮጵያ ተወደው ተከብረው ገድልና ድርሳን እየተደረሰላቸው ሲመሰገኑ ከልዮን ዠምሮ ሁለት ባሕርይን የሚከተሉት ሊቃነ ጳጳሳት ተነቃፊዎች ናቸው ።

አንድ ባሕርዮች ሁለት ባሕርዮችን እላይ በተመለከትናቸው የጽርፈት "ስድብ" ቃሎች እየሰደቡ ስማቸውን ሲያጥፋፉ በሁለት ባሕርዮች ዘንድ ደግሞ እንደዚሁ አንድ ባሕርዮች በቋንቋቸው (HERETIQUES) መናፍቃን (SCHISMATIQUES) በራሳቸው የተወገዙ" እየተባሉ ይሰደባሉ (4)። ከዚያ ወዲህ የተነሡ የካቶሊክ ካህናት በጻፉት መጻሕፍት ውስጥ ስለኢትዮጵያ ነገሥታትና ጳጳሳት የቤተ ክህነት አለቆች ሲጽፉ "መናፍቁ ንጉሥ መናፍቁ አለቃ መናፍቁ ጳጳስ" እያሉ ነው የሚጽፉት (5) ።

መቼም በዘመኑ የነበረውን መንፈስ ካዬ ገላውዴዎስ እስቸጋሪ ዘመን ጋር ለማመዛዘን እንዲጠቅም ስንል ወደዚህ ዝርዝር የሃይማኖት ጉዳይ ገባን እንጂ ለደግ ነገር በመጣው በክርስትና ሃይማኖት የ፲፮፻ዐ እንኳን በጉባኤ መደባደብ እንደደንቡ ስድቡ ራሱ ነውር መሆን ነበረበት ።

ፍቅርን ርኅራኄን ደግነትን አዲስ የደኅንነት ሕይወትን መሠረት አድርጎ የመጣው ክርስቶስ የመሠረተውን ሐዋርያት ሰማዕታት ሕይወታቸውን የሠዉበትን ሰላማዊ የክርስትናን ዓላማ ይኸን የመሳሰለ የስድብ ቃል እየጨመሩ ከመሠረቱ እያወጡ ማበላሸት ባልተገባ ።

ነገር ግን ዘውድም ቢደፉ ቆብም ቢያጠልቅ የማዕርጉ ሥያሜ ንጉሥ ቢሆን ጳጳስ በማንም ሰው ላይ ያለውን መልካም ባሕርይ ተመራማሪ እእምሮውን ርኅሩኅ ሕሊናውን ባንድ ወገን ንዴት ግልፍታ ብስጭት ቁጭት ቂምና በቀል ገብቶ ስለሚበርዝበት ወይም ስለሚመርዝበት በየጊዜው በየምክንያቱ ይኸን የመሳሰለ ጠብ በሰው ልጆች መካከል የማይቀር ሆኖ እስከ ጊዜያችን ድረስ ከዘለቀ በኋላ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ ያንን ሁሉ የስድብና የጠብ ጊዜ ወደ ጐን አድርገው የቤተ ክርስቲያን

(1) እርሱም የቂሣርያ "ቂሣርያ አዲሱ" ኤጲስ ቆጶስ ነው

(2) ዮሐንስ አፈ ወርቅ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት

(3) ቄርሎስ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከዲዮስቆሮስ በፊት ንስጥሮስን የረታው ፡ መዝገበ ሃይማኖት ቹሩሊ ያሳተመው ገጽ 143 ተመልከት ።

(4) Histoire du christianisme-La croze ገጽ 157

(5) I miei 35 anni di missione nell alta Etiopia. G. MASSAIA vol. 9. ምዕ.1 ገጽ 3- 13 ምዕ. ቍጥር 9Vol. II ምዕ. 5

አለቆች በፍቅርና በሰላም ለመቀራረብ በመታገላቸው ያስመሰግናቸዋል ።

እንግዲህ እንደዚህ ሆኖ ከአብርሃ እስከ ገላውዴዎስ ድረስ ከሺ ዓመት ይበልጥ ተመሥርቶ የጸናውን የተዋሕዶ ሃይማኖት ባንድ ጊዜ ወደ ሁለት ባሕርይ ለመለወጥ በፊት ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በከንቱ የደከመውን ወደፊትም ፓትሪያርክ ተብሎ የመጣው አንድሬያ አቪዬዶ በዚሁ መሥመር ሲደክም እንመለከታለን ።

ነገር ግን ይኸን ባንድ ባሕርዮችና በሁለት ባሕርዮች መካከል ያለውን የከረረ ጠብ አንድ ሌላ የእስላም ሃይማኖት ኃይል ከዓረብ አገር ተነሥቶ እኛንም በአገራችን እነርሱንም በአውሮፓ በመካከለኛው ምሥራቅ ሲያስፈራቸው ጠቡን ትተው ለመቀራረብ ከፍሎራንስ ጉባኤ ዠምሮ ተሞክሯል ። ከዚህ በፊት በምዕራፍ ፲፭ እንደተመለከተው የእስላሞች ነቢይ መሐመድ እንደአውሮፓ ቍጥር በ፭፻፸ ዓ.ም. በተናቀውና በበረሃማው አገር በሜካ ተወልዶ አድጎ ቍራንን አስተምሮ የእስላምን ሃይማኖት ከክርስትና ሃይማኖት ለየት አድርጎ "አላህ አንድ ነው" ብሎ መሠረተ ። በርሱም ዘንድ የአምላክ በአካል ሦስትነቱ ከሦስቱ አንድ አብ ወላዲ ሁለተኛው ወልድ ተወላዲ ሦስተኛው መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ የተባለው የክርስቲያኖች እምነት ተነቀፈ ። መሐመድ በመሠረተው ሃይማኖት ውስጥ የአምላክ ሥጋ ለብሶ መወለዱ መሞቱ ስለተካደ ሥጋና መለኮቱ የተዋሐደ አንድ ባሕርይ ወይም ያልተዋሐደ ሁለት ባሕርይ የሚባለው ረቂቅ ክርክርና ጠብ በፍጹም ስለሌለ እርምጃው በተለይ በአረማውያን ዘንድ[illegible]ቋላሉ ተስፋፋ ።

ስለዚህ ይህ መሐመድ የመሠረተው የእስላም ሃይማኖት መሐመድ ከሞተ በኋላ ተከታዮቹ እነከሊፋ ኡመር . . . . . . መካከለኛውን ምሥራቅና የአፍሪካን ሰሜን ወርረው ይኸንኑ ሃይማኖት ሲያስፋፉ ይኸው የእስላም ሃይማኖት በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አብዛኛው በንግድ ምክንያት ከዓረብ አገር በመጡ እስላሞች አማካይነት እየገባ መስፋፋት ዠመረ ።

በዚህ ጊዜ ተዋሕዶዪቱ ኢትዮጵያ በማትቀበለው የካቶሊክ ጐራ ፊት በግዛቷ ውስጥ ሌላ የሚቃወማት የእስላም ጐራ ተፈጥሮ ከቀን ወደቀን እያስፈራ እየከበደ ለኑሮዋ ችግር ፈጠረባት ። ቀድሞ የሃይማኖት ጓደኞች ወይም ወንድሞች የነበሩት ግብጾችና የኑብያ ሕዝቦች ከዚህ ከዓረብ ወረራ ወዲህ አብዛኛዎቹ ወደ እስልምና ተለውጠው ጥቂቶቹ ብቻ ስለቀሩ ባለፈው ሁሉ እንደተመለከትነው የግብፅ መንግሥት ከሌሎቹ የዓረብ መንግሥታት ጋር በኢትዮጵያ ያሉትን እስላሞች እየደገፈ መሣሪያም ሲሰጥ ኢትዮጵያ የውጭ ድጋፍ ወደ መፈለግ ስታዘነብል በአሁኑ ሰዓት ድጋፍ ሊሆኑ የሚችሉት በመስቀል ጦርነት የእስላምን ኀኸርነት የተቃወሙት እነዚያ እምነታቸውን የማትቀበለው የአውሮፓ መንግሥታትና የሮማ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት ሆነው ተገኙ ።

ኢትዮጵያ በመሬት አቀማመጥ በዘርና በልማድ በቋንቋ ከሚቀርቧት ጎረቤቶቿ ጋር በክርስትናና በእስላም እምነት ምክንያት ስትለያይና ችግር ሲገጥማት አሁን ደግሞ በክርስቶስ አንድ ባሕርይና ሁለት ባሕርይ ምክንያት ተጣልታ ከተለያየቻቸው የአውሮፓ መንግሥታትና የሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጋር መልሶ መወ

ዳጀት ግዴታ ሆነ ።

ስለዚህ ባለፉት ምዕራፎች እንዳነበብነው የኢትዮጵያ መንግሥትና የፖርቱ ጋል መንግሥት ከሮማ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመስማማት ተወዳጅተው ይህ አሁን ከግራኝ አህመድ ጋር ለመዋጋት የቻለው የፖርቱጋሎች ርዳታ መምጣት ቻለ ። የመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች በእንዴት ያለ አኳኋን በእንዴት ያለ መሥዋዕትነት እንደተዋጉ በእንዴት ያለ የፍቅር ስሜት እነካስታንሆዞ ከገላውዴ ዎስ እየተሰናበቱ መመለሳቸውን አንብበናል ።

በፈቃዳቸው የቀሩት ፩፻፳ ፖርቱጊዞች ደግሞ ሰፋፊ መሬት ርስትና ጉልት እየተሰጣቸው በሹመት እንደማዕርጋቸው ተደልድለው ንጉሠ ነገሥቱን ዓፄ ገላው ዴዎስን እያገለገሉ ለመኖር ቆርጠው ባገሩ ላይ ይገኛሉ ። ስለዚህ በነርሱና ባፄ ገላውዴዎስ መካከል ያለው ግንኙነት ምንም ዓይነት የኑሮ ችግር አልፈጠረም ። ችግሩ የተፈጠረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊክ ሆና በሮማ ቤተ ክርስቲ ያን ሥር ትተዳደር እኔም ለዚች ቤተ ክርስቲያን የመዠመሪያው ጳጳስ ልሁን ብሎ በተነሣው በዮሐንስ ቤርሙዴዝ ምክንያት ነው ። ሁኔታውን በሚቀጥሉት ምዕ ራፎች እስክናነብ ድረስ በመካከሉ ንጉሡ ገላውዴዎስ ከአባስ ጋር ያደረጉትን ጦር ነት በቅድሚያ እንመልከት ።

ISIC

### ምዕራፍ ፻፴፬

### በወጅ ያፄ ገላውዴዎስና የወዚር አባስ ጦርነት (፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ጥቅምት)

ካስታንሆዞ ከሃምሳ ፖርቱጋሎች ጋር ሲመለስ ፩፻፳ የሚሆኑ ፖርቱጋሎች ከርሳ ቸው ጋር መቅረታቸውን የነርሱም አለቃ ማርቆስ ተብሎ የተሠየመው አርያስ ዲያዝ መሆኑን ከዚህ በፊት አንብበናል ። እንደ ዓረብ ፋቂህ የመሰለ ጸሐፊ ከግራኝ ወዲህ ያለውን ያፄ ገላውዴዎስን ዘመን ታሪክ በዝርዝር የጻፈው የውጭም የአገር ተወላጅም ጸሐፊ ስለሌለ በአሁኑ ሰዓት ከባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በቀር በንጉሡ ዙሪያ ያሉት የጦር ሹማምንትና መኳንንት በደንብና በተጣራ መንገድ አናውቃቸ ውም ። ካስታንሆዞ የመስቀል በዓል ለት አዛዥ ዶጋላያ ትልቅ ሰንደቅ ዓላማ ይዞ በፊታቸው ይሄድ ነበር ብሎ ስለጠቀሰ ይህን የሚለው ሰው አዛዥ ደገልሃንን ይሆን የሚል ጥርጣሬ አለ ።

ስለዚህ በጠቅላላው ዓረብ ፋቂህ ጽሑፉን ካቆመበት በጣና ሐይቅ ከደብረ ገሊላ ብዝበዛ ወዲህ በተደረጉት ጦርነቶች የሞቱትንና ተርፈው በአሁኑ ሰዓት ባፄ ገላውዴዎስ ውስጥ ሆነው የግራኝን ትራፊ ጦር በያለበት በተለይ በደቡብ ክፍል በሸዋ በፈጠጋር በደዋሮ በባሌ በወጅ በገንዝ በእናሪያ በጉራጌ ያለውን ጦር ለመደ ምሰስ የተሰበሰቡትን ከአፈወ ድንግል ከሐመልማልና ከፋኑኤል በቀር የቀሩትን ስለማናውቅ መኖራቸው መዋጋታቸው ዠብዱ እየሠሩ መሞታቸው ሳይቀር ካለ መጻፍና ካለመታወቁ የተነሣ የሁሉንም አገልግሎት በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ አገል

ግሎት ላይ ብቻ ደርቦ ለመመልከት ግዴታ ሆኗል ።

በአሁኑ ሰዓት ከግራኝ ሞት ወዲህ በደቡብ ክፍል ጦር ሰብስቦ ዓፄ ገላውዴዎስን ሊቋቋም የተዘጋጀ ወዚር አባስ ነው ። ይህ ሰው በዚህ በግራኝ አህመድ የወረራ ዘመን የሠራውን እንባቢ እንደሚያስታውሰው እምናለሁ ። የዘነጋ ቢኖር እንደገና በዚህ ተዋግቶ በሞተበት ምዕራፍ እንደገና ለማስታወስ ያህል ወደኋላ ተመልሰን አጭር ታሪኩን እንጠቅሳለን ።

አባስ የግራኝ አህመድ ወንድም የገራድ አቡን ልጅ ነው ፤ አባቱ ገራድ አቡን ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር ሲዋጋ ሞቷል ። በዚህ ምክንያትም ወሰን ሰገድ በውጊያ ከመሞቱ በፊት ለግራኝ በጻፈው ደብዳቤ ላይ «ታላቅ ወንድምህን ገራድ አቡንን የገደልሁ እኔ ነኝ» ያለውን እናስታውሳለን ። ልጁ አባስም በይፋት ከአውራይ አቡን ጋር ራስ ነቢያትን ወግቷል ፤ በደዋሮና በባሌም ከስመ ጥሩው ዝግና ከአዝማች አዳሉ ጋር በግድም (ግድምኔ) ከራስ ደገልሃን ልጅ ከተክለ ሃይማኖት ጋር ብዙ ጊዜ ተዋግቷል ። መዠመሪያ የሹመት ስሙ ገራድ ነበር ። ቀጥሎ ደግሞ ግራኝ ወደ ትግሬ ዘምቶ ባስገበረበት ወቅት የባሕር ነጋሽነትን ሹመት ይዟል ። ከዚያ ቀጥሎ ወዚር አዶሌን ተስፋ ልዑል ከገደለው በኋላ ብዙ የእስላም ጦር ይዞ የእስላሞቹን ሹማምንትና ከዳተኞቹን እነተስፋዊን አስከትሎ ተስፋ ልዑልን ተዋግቶ የገደለ ወዚር አባስ ነው ። በቤገምድርም የተረፈውን ያፄ ልብነ ድንግልን ጦር እየወጋ ብዙ አገር አሳምኗል ISIC

ስለዚህ ወዚር አባስ ግራኝ በሕይወት በነበረበት ጊዜ በተለይ ከወዚር አዶሌ ሞት በኋላ በዝምድናውና ባገልግሎቱ ጭምር ለግራኝ ተከታዩና ምክትሉ ነበረ ማለት ነው ። አብዛኛ ጊዜ በሹመት ይዞት የነበረው አገር መዠመሪያ ግድምን ፤ ቀጥሎ ትግሬን (ሠራዌን) ከዚያ በመጨረሻ ግራኝ በሞተበት ጊዜ ከቤገምድር ጀምሮ እስከ ኑብያ ወሰን ያለውን አገር ይገዛ ነበር ።

ግራኝ ከሞተ በኋላ በስሜን በኩል በትግሬና በቤገምድር በጐጃም አውራጃ የሚገኙት አገሮች ሁሉ ላፄ ገላውዴዎስ ተባብረው ስለተገዙ ባንድ ወገንም የዋናው የግራኝ አህመድ ሞት ተስፋ ስላስቆረጠው ከሰሜኑና ከምዕራቡ ኢትዮጵያ ተከታይ ወደሚያገኝበት ላገሩ ለአዳል ወደሚቀርበው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ተዛውሮ ያን ጊዜ ታላላቅና ስመ ጥሩ የሆኑትን የኢትዮጵያ አውራጃ የሆኑትን ባሌን ፤ ፈጠጋርን ፤ ደዋሮን እንደ አንድ መንግሥት አድርጎ ራሱ እንደ ንጉሥ ሆኖ ማስተዳደር ዠመረ ። በዚህ ምክንያት ዓፄ ገላውዴዎስ የሰሜኑንና የሰሜን ምዕራቡን ክፍል ከአደላደሉ ወዲህ ይህ አባስ የያዘው የባሌና የፈጠጋር ፤ የደዋሮ ግዛት አባቶቻቸው ሲሾሙበት ሲሸሩበት የኖሩበት ያንዲት የኢትዮጵያ ግዛት በመሆኑ እነዚህኑ አውራጃዎች ወደ ኢትዮጵያ መጠቅለልና ማሳመን ዋና ተግባራቸው ስለሆነ ከግራኝ ሞት ወዲህ የቤገምድርን ፤ የላስታን ፤ የትግሬን ግዛት በመሰብሰብና በማዋሐድ የ፲፭፻፴፯ - ፴፰ ዓ. ም.ን ጊዜ ካሳለፉ በኋላ በአሁኑ ሰዓት ከወዚር አባስ ጋር ለመዋጋት ወደ ደቡቡ ክፍል በተለይ ያን ጊዜ ከታላላቆቹ አውራጃዎች ወደሚቆጠረው ወደ ወጅ መጥተዋል ።

የመጡትም በ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. የመስቀልን ፤ የልደትን በዓል በላስታና በትግሬ አገር አክብረው እንካስታንሆዞን ካሰናበቱ በኋላ የክረምቱን ወራት በዚያው አሳልፈው በ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. ክረምቱ ሲወጣ ጉዞ ጀምረዋል ማለት ነው ።

በበኩሉ አባስ እርሳቸው የሰሜኑን ክፍል ሲያቀኑ እርሱ ግራኝ ከሞተበት ጦርነት የሸሸውን ጦርነቱን ካልተካፈለው ጋር አዋሕዶ ያጐቱን የግራኝ አህመድን ገዳይ ተዋግቶ ለመበቀል ይኸን የሁለት ዓመት ጊዜ ለዝግጅት ተጠቅሞበታል ። ስለ አባስ ጦርነት ታሪክ ነገሥቱ ባንድ ቦታ ላይ ባጭሩ «ግራኝ በሞተ በ፲ኛው ዓመት አባስን ገደለ» ብሎ ካለፈ በኋላ በሌላ ሥፍራ ላይ ሰፋ አድርጎ የሚያመጣውን ወደ ምዕራፉ መጨረሻ ላይ እንመለከታለን (1) ።

ስለ አባስና ስለ ዓፄ ገላውዴዎስ ጦርነት የምናገኘው ጥቃቅን ምንጭ ከቤርሙዴዝና ከታሪከ ነገሥቱ ነው ። እንደ ጦርነቱ ትልቅነት ሁለቱም የውጊያውን ታሪክ በሰፊው አልዘረዘሩም ።

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ እንደሌሎቹ የፖርቱጋል ጸሐፊዎች የአገርም የሰውም ስም በጣም ይሳሳታል ። ገላውዴዎስን ገራዴውስ ግራኝን አንድ ቦታ ላይ ጐርንሃ በሌላ ቦታ ላይ የዘይላው ንጉሥ ነው የሚለው ። በዚህ ዓይነት ወዚር አባስን በምን አኳኋን እንዳዛመደው ሳይታወቅ የአደን ንጉሥ ይለዋል ። ምናልባት ከግራኝ ሞት በኋላ መተካቱን በማመን የአዳል ንጉሥ ማለቱ ይሆናል ።

ታሪኩንም ሲጀምር ከትንሽ ጊዜ በኋላ ንጉሡ የማሮን የዩዋ (ሸዋ) የግድምን የጐጃምን ግዛታቸውን ለማሳመን ገብ ለማድረግ ቆርጠው መነሣታቸውን ከሁሉ በፊት ጦርነቱን ትልቅና ሀብታም በሆነው በሸዋ ወሰን ላይ መጀመራቸውን ..... ከዚያ የጽዮን ገዳም በሚባል አገር ደርሰው ሳለ የዚህ አገር ረዥዥም ሰዎች ለግራኝ ታማኝ ሆነው ስለተቋቋሙ የተከተሏቸው ፖርቱጊዞች በመድፍና በጥይት ተዋግተው ሁሉንም ንጉሡ እንዳሳመኗቸው በዚሁ ሳሉ ከዚሁ የአደን ንጉሥ ከሚለው ከአባስ «ግራኝ ሞተ ብለህ እንዳታስብ (2) በርሱ እግር እኔ ተተክቻለሁ ። በከንቱ የማስፈራራ ለፍላፊ ፈሪ እንዳልመስልህ መጥቼ እጐበኝሃለሁ» የሚል መልእክት ለዓፄ ገላውዴዎስ መላኩን ያረጋግጣል ።

ከዚሁ እያይዞ ንጉሡ ከነሠራዊታቸው ሲጓዙ ከትልቅ ወንዝ ላይ እንደደረሱ (3) ወንዙን ለመሻገር ብዙ በሬ ታርዶ በታረደው በሬ የቆዳ ጀልባ ተሠርቶ ከማዶ በገመድ እየተሳበ ሠራዊቱ በዚያ ሌሊቱን ሲሻገር ፈረሶቹ ደግሞ በራሳቸው እየዋኙ ለጠላት ሠፈር የምዕራፍ አጋማሽ በሆነው ሥፍራ ላይ በሽሽግ ተሻግረው በዚያው ሌሊት ጦርነቱ መጀመሩን ብዙ እስላሞችና አባስ ራሱ መሞታቸውን ፤ ከወዲህም ብዙ ክርስቲያኖች መሞታቸውን ፤ ንጉሡ ገላውዴዎስም በዚሁ ሰው ለሰው በግጊ

(1) ወእምድኅረ ሞተ ግራኝ በ፲ ዓመት ቀተሎ (ገላውዴዎስ) ለአባስ ። ረኔ ባሴት ያሳተመው ታሪከ ነገሥት ገጽ 334 ።

(2) ደስ እንዳይልህ ያለውን ይሆናል እንዳታስብ የሚለው ።

(3) የአዋሽ ወንዝ መሆን አለበት ።

ተያይበት የድንግርግር ጦርነት ቆስለው እንደነበር ፤ እስላሞቹ የንጉሣቸውን የአባስን መሞት ሲያዩ ስለሸሹ ፖርቱጋሎች እያባረሩ ብዙዎቹን መፍጀታቸውን ፤ ሲመለሱም የአባስን ሚስት ማርከው ይዘውላቸው እንደቀረቡ ፤ ንጉሡም ስላገኙት ድል እነሱንም አምላካቸውንም አመስግነው የአባስን ፈረስና ሰይፍ ብቻ ሲያስቀሩ የቀረውን ቍጥሩ የበረከተ የተማረከ ሀብት የጦርነቱን ድል ላስገኙት ለፖርቱጋሎቹ በወንድማማችነት እንዲካፈሉት መፍቀዳቸውን ምርኮኛዪቱን ንግሥት ስሚደኒያ እምባራ የምትባለውን (1) ክርስትና መነሣት የፈቀደች እንደሆነ የፖርቱጋሎቹ መሪ አሪያስ ዴዝ እንዲያገባትና እርሱም የርሷ ግዛት የነበረውን የደዋሮንና የባሌን ግዛት ይግዛ ብለው መፍቀዳቸውን በማከታተል ቤርሙዴዝ ታሪኩን እዚህ ላይ ያቆማል (2) ።

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የዚህን ጦር ከመዠመሪያ እስከ መጨረሻ የጦርነቱን ድል እንዳለ ጠቅሎ ለወገኖቹ ለፖርቱጋሎቹ ሰጥቶታል ። ነገር ግን ምንም እንኳን ፖርቱጋሎቹ የጠበንጃ መሣሪያ በእጃቸው ስላለ ለውጊያውም ለድሉም ዓይነተኞች ቢሆኑ እነርሱ በጥይት ጦርነቱን ሲከፍቱት በጐራዴና በሰይፍ በጦር እየተዋጉ የሚገድሉትና የሚሞቱት የኢትዮጵያውያኑ ቍጥር በጣም እንደሚበረክት የታወቀ ነው ። ነገር ግን ቍጥራቸውንና ስማቸውን በዚህ ምዕራፍ ላይ ለማውሳትና ሕያው ለማድረግ እንኳን በባዕዱ በቤርሙዴዝና ባገሩም ታሪከ ነገሥቱን ባዘጋጀው ብርዕ ስለ አልተጠቀሱ የብዙ አገልጋይ የሕይወት ታሪክና ዝ ብዱ እንደተደፈነ መቅረቱን ሁል ጊዜ በጸጸት እንመለከታለን ።

ISIC

በበኩሉ የዚህኑ የጦርነት ታሪክ ታሪከ ነገሥቱ ባንድ ቦታ ላይ ግራኝ አህመድ በሞተ በሁለተኛው ዓመት ላይ ዓፄ ገላውዴዎስ አባስን መግደላቸውን አውስቶ ካለፈው የተለየ ሌላ የታሪከ ነገሥት ጽሑፍ በተለይ ጕንዘልማን ያሳተመው የራሳቸው ዜና መዋዕል ከዚህኛው ትንሽ ረዘም አድርጎ እንደዚህ ይላል «በዚህ ዓመት ወዚር አባስ ባሌ ፈጠጋር ደዋሮ በሚገኙት እስላሞች ላይ ነግሦ መቀመጫዬን በአርዮብ (3) ዙፋኔን በደቡብ አገሮች ላይ አደርጋለሁ ብሎ በትምክህት በገላውዴዎስና በፈጣሪው ላይ ጽርፈት አብዝቶ ተናገረ (4) ። ንጉሡ ገላውዴዎስ ግን ባለፈው በሠራለትና ስሙ በተባረከው ተማምኖ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች በዮርዳኖስ ማዶ ሆኖ ጠላቶችን ያጽናና በነበረው ዓይነት ሕዝቡን እያጽናና ሦስት የክረምትን ወራት

(1) ስሚን ከግራኝ ባለቤት ከድል ወንበራ ጋር ያማታው ይመስላል ።

(2) ባሌንና ደዋሮን የርሷ ግዛት ማለቱ የባሏ የአባስ ግዛት የነበረ መሆኑን ለማመልከት መሆን አለበት ። ዶሮሮ የሚለውም ደዋሮን መሆን አለበት ። Hist. du christianisme... ገጽ 176 - 181

(3) አርዮብ ምን እንደሆነ አይገባም ያንድ አገር ወይም የከተማ ስም ይሆናል ፤ ወይም አርያም ማለቱ ይሆን ?

(4) ታሪከ ነገሥቱ ይኸን ቃል የሚጠቅሰው አባስ ለዓፄ ገላውዴዎስ የማስፈራሪያ ቃል መላኩን በቤርሙዴዝ ጽሑፍ ላይ ያነበብነውን ይሆናል ።

በጠላቱ ላይ ታግሦ . . . . . ከኢትዮጵያና ከግብጽ በሁለተኛው ወር ሠኔ ወጅ ሄደ (1) ። ወዚር አባስም ይኸን ሲሰማ መኳንንቱንና ሠራዊቱን ይዞ ሲመጣ ገላው ዴዎስ ልቡን አጽንቶ እንደ ሠርገኛ ተቀበለው . . . . . . ጦርነቱም ተገኘመረ ። አባ ስና መኳንንቱ በብረት እየተመቱ ወደቁ በዚያን ጊዜ አሞሮች የርሱንና የመኳንን ቱን የፈረሶቻቸውን የአገልጋዮቻቸውን ሥጋ ለመብላት እንደ በዓል ቀን ተሰበ ሰቡ . . . . . . እንደዚህ አድርጎ ድል ከአደረገ በኋላ ወተትና ማር የሚያፈሰውን የተባረከ አገር ለሕዝቡ አወረሳቸው» እያለ በራሱ በዘመኑ የግዕዝኛ አነጋገር ከመ ንፈሳዊ አሳብ ጋር በማያያዝ ተርኮ ይፈጽማል (2) ።

ጦርነቱ የተደረገበትን ቦታ ታሪከ ነገሥቱ ወጅ እንዳለው ተመልክተናል ። ይህ አገር በአሩሲና በጉራጌ በገንዘ መካከል በዛሬው የየረርና የከረዩ ግዛት የአ ዋሽ ወንዝን ተሻግሮ የዛሬው የወንጂ የሱካር ፋብሪካ ያለበት ቀበሌን ሁሉ ጠቅ ልሎ ያለው ነው ። ጽሑፉ ሁሉ አንዱ ወጅ ሲለው ሌላው ዋጅ ይለዋል ። የዛሬው ወንጂ ከዚያ ስም ተያይዞ የመጣ መሆን አለበት ።

በግራኝ የወረራ ጊዜ ካሄ ልብነ ድንግል ተሾሞ የዚህ አገር አስተዳዳሪ የነበ ረው እስላም ደሀር ይባል እንደነበረ እርሱም የዓፄ እስክንድር አማች እንደነበረ እስላም ደሀርንም ወዚር ሞጃሂድ አስገብሮ ግዛቱን እንደያዘበት ባለፈው ያነበብ ነው ትዝ ይለናል ።

እንደዚሁም ደብረ ሊባኖስ ከተቃጠለ ራ፲፭፻ሮስን ሰገድ ከሞተ ወዲህ ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል ተስፋ በመቁረጥ የሸዋን ክፍል ደቡቡን ግዛታቸውን ለቀው ወደ ቤተ አምሐራ ሲዛወሩ የተነሡት ከዚህ ከወጅ ነው ። በፊትም ከግራኝ ለመዋ ጋትም ሆነ እንደዚሁም ለማለፍ የአዋሽን ወንዝ እርሳቸውም ሠራዊታቸው ይሻ ገሩ የነበረው ከበሬ ቆዳ በተሠራ በብዙ የቆዳ ጀልባ መሆኑን ከዚህ በፊት ያነበብ ነው አሁን ቢርሙዴዝ ከጻፈው ጋር ገጥሟል ።

የሆነ ሆኖ ከዋናው መሪ ከግራኝ አህመድ ውድቀት ወዲህ የዚህ የወዚር አባስ በወጅ መሞትና የሠራዊቱ መፍረስ ላፄ ገላውዴዎስ መንግሥት አመሠራረት ሁለ ተኛና ታላቅ ድል ነው ። ከአባስ ሞት በኋላ ሁሉም ወደ ሐረርጌ እየሸሸ በግራኝ አህመድ ሚስት በድል ወንበራና ከአባስ በኋላ በተነሣው በሙጃሂድ ልጅ በኑር መሐመድ ዙሪያ ተሰበሰበ ። ዓፄ ገላውዴዎስ ከርሱ ጋር ያደረጉትን የሕይወታ

(1) በግብፅና በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥቅምት ፪ኛ ወር ነው ።

(2) ወበእማንቱ መዋዕል ነግሠ ወዚር አባስ ላዕለ ተንባላት እለ ሀለዉ በባሊ ፤ ወበፈጠጋር ወበደ ዋሮ . . . . . . . መበካልእ ወርኅ እምአውራኅ ኢትዮጲስ ውእቱ ወበጠሩ ሳብዕ እም አውራኅ ዕብራዊት በጽሐ ንጉሥ ገላውዴዎስ ምድረ ወጅ ። ወዘንተ ሰሚዖ ወዚር አባስ ተንሥአ እምድር ዘንበረ ምስለ ኵሉሙ ዓበይቱ . . . . . ወንጉሥኒ ገላውዴዎስ ኮነ ይጸንሕ ተቀብሎቶ ከመ ቀበለ መርዓዊ . . . . . ወወጽአ ወሞዓ ወወድቀ አባስ ወኵሎሙ መላእክቲሁ በሐዊ . . . . . . የገላው ዴዎስ ዜና መዋዕል ጉንዘልማን ያሳተመው ገጽ 28 – 30

ቸው ፍጻሜ የሆነበትን ጦርነት ከመመልከታችን በፊት በርሳቸውና በቤርሙዴዝ የተነሣውን ሃይማኖታዊ ጠብ በሚከተሉት ምዕራፎች እናንብብ ።

## ምዕራፍ ፻፴፭
## በዮሐንስ ቤርሙዴዝና ባዬ ገላውዴዎስ መካከል የተቀሰቀሰው የመጀመሪያው ጠብ

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ አገሩ ጋሊስ (ኤስፓኝ) ውስጥ ነው (1) ። ከስታንሆዞ የቀድሞ የቤርሙዴዝ ሥራው ጠጉር ቆራጭ ነበር ማለቱን ከዚህ በፊት አንብበናል (2) ። ከሮድሪግ ደሊማና ከነአልቫሬጽ ጋር በ፲፭፻፲፱ (፲፭፻፳፮) ዓ. ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እነሱ ወዳገራቸው በ፲፭፻፲፰ ዓ. ም. (፲፭፻፳፭) ሲመለሱ እርሱ ቀርቶ በ፲፭፻ ፳፯ ዓ. ም. (፲፭፻፴፭) ዓ. ም. ርዳታ አፋጥኖ እንዲያመጣ ካዬ ልብነ ድንግል ወደ ሮማ ሊቃነ ጳጳስ ወደ ቀሌምንጦስ ፯ኛና ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ወደ ዮሐንስ ፫ኛ ተልኮ መሄዱን በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. (፲፭፻፵፩) ዓ. ም. የጦሩን ርዳታ ይዞ መጥቶ ከምጥዋ ዠምሮ እስካሁን ድረስ ያደረገውን ሁሉ አንብበናል ። አሁን ደግሞ ወደኋላ ተመልሰን ግራኝ ከመሞቱ በፊት ዠምሮ ያነሣውን ክርክር እናነባለን ።

ቤርሙዴዝ ካስታንሆዞን ቀድሞ ጠጉር ላጭ ይበለው እንጂ በቅርብ የሚያውቀው ፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ሐኪም(PHISICO MESTRE) እንደሚለው አንብበናል (3) ። ምናልባት ቀድሞ በወጣትነቱ ጊዜ ጠጉር ላጭ ሆኖ በኋላ ከዚሁ ከጠጉር ቆራጭነትና ከንጽሕና ጋር የተያያዘ በዚያው የሕክምና ሥራ ዠምሮ ሠርቶ ይሆናል ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የቤተ ክህነት አስተዳደሩና የመንፈሳዊ መጽሐፍ ዕውቀቱ መጠነኛ መሆኑን ጸሐፊው ሁሉ ተስማምቶበታል ። እርሱ ራሱ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ወደ ሮማ ከመላኬ በፊት ንጉሡ ዓፄ ልብነ ድንግል አክብረው አስቀምጠውኝ እንዲያውም በዙፋን የተከተላቸውን ልጃቸውን ገላውዴዎስን ክርስትና አባት ሆኜ እንዳነሣ ፈቅደው አነሣሁ ይላል (4) ።

ከዚሁ በማያያዝ ዓፄ ልብነ ድንግል ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ አርጅተው ከሞት አፋፍ ላይ ስለነበሩ በእርሳቸው እግር እኔ ያገሪቱ ጳጳስ እንድሆን ፈቅደው ጳጳሱም እሺ ብለው የጵጵስናውን ሥፍራ ቢሰጡኝ መዠመሪያ ይህ ሹመት በሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት መጽደቅ አለበት ብዬ የንጉሡን ደብዳቤ ይዤ ወደ ሮማ ሄድሁ ብሎ በራሱ መጽሐፍ የተረከውን ባለፈው ያነበብነው ትዝ ይለናል ።

ይሁን እንጂ ዓፄ ልብነ ድንግልና ግብፃዊው ጳጳስ ምንም የግራኝ ወረራ ከሥጋት ላይ ቢጥላቸው ወዲህ ካቶሊክ ወዲህ ከዚያው ከነርሱ ጋር እነፍራንቼስኮ

(1) Hist. du Christ... ገጽ 89 - 90
(2) የፖርቱጋሎች ዠግንነት ገጽ 14
(3) VERDADEIRA ምዕ. 82
(4) Histoire du Christ... ገጽ 263

ከተመለሱ ዠምሮ የተቀመጠውን ተራ የፖርቱጋል ተወላጅ በኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ላይ ባንድ ጊዜ ጳጳስ ብለው ሊሾሙት የሚችሉ አይመስልም ። ቢሾሙ ትም ሕዝቡም ቤተ ክህነቱም እንደማይቀበል የታወቀ ነው ። የሆነ ሆኖ እውነተኛ ውን ለመረዳት ይኸን የርሱን ጽጽስና ሊያስረዳ የሚችለውን ያዔ ልብነ ድንግልን ደብዳቤ ዋናውንም ትርጉሙንም ተፈላልጊ እኔም አላገኘሁት ማንም ጸሐፊ እስካ ሁን በጽሑፉ አስፍሮ የገለጠው የለም ወይም እኔ አላየሁም ።

የግራኝ ወረራ በሚያዋክበት ሰዓት በ፲፭፻፳፯ ዓ. ም. ከዔ ልብነ ድንግል ዘንድ ተልኮ ሊስቦንም ሮማም ደርሶ ለንጉሡም ለጳጳሱም የኢትዮጵያን ጵጵስና ከንጉሡ ከልብነ ድንግልና ከጳጳሱ ከአባ ማርቆስ ተቀብያለሁ ብሎ ስለነገራቸው በዚሁ በጳጳስ መልክ ለጊዜው ተቀብለውት ነገር ግን ሰውዬው በቂ የቅስና ትምህ ርት ስለሌለው የሮማ ሊቀ ጳጳስ እርሱ ተቀበልሁ ያለውን የጵጵስና ደረጃ ለሌላ ሰው ሊሰጡና ሊልኩ አሳብ እንደነበራቸው ባንዳንድ ጽሑፍ ይገኛል ።

እርሱ በጻፈው መጽሐፍ ላይ የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፫ኛ ከኢትዮ ጵያ ይገቱ የመጣሁትን የኢትዮጵያን የጳጳስነት ሹመት ብቻ ሳይሆን የእስክንድ ርያ ፓትሪያርክነቱን ሾመውኝ ነበር ብሎ በመጽሐፉ የተረከውን የዛሬ ጸሐፊዎች በቫቲካኑ ቤተ መዛግብት ተፈላልገው የርሱን የፓትሪያርክነት ሹመት የሚያጸ ድቅ አንድም ሰነድ አለማግኘታቸውን ገልጸዋል (1) ። ስለዚህ ሮማ ሄዶ ከኢትዮ ጵያ ጵጵስና ተሾሚያለሁ ። ወደ ኢትዮጵያ ሚ፯፻፸ ጳጳስነቱ ከሮማ ሊቀ ጳጳሳት ጳጳ ቀልኝ እያለ በርሱው ዘዴና ውሸት የተገነባ ሹመት እንጂ መሠረት የያዘ አይደ ለም የሚሉ ጸሐፊዎች ሞልተዋል (2) ።

የሆነ ሆኖ የሮማ ሊቀ ጳጳስም የፖርቱጋል ንጉሥም አጥብቀው የሚመኙት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከተዋሕዶ ጉራ ስቦ ወደ ካቶሊክነት ለማስገባት እንጂ የኢትዮጵያ ንጉሥና ጳጳስ ተስማምተው ከሾሙት ምንም እንኳን ትምህርቱ የቤተ ክህነት አስተዳደጉ ለዚህ ደረጃ የሚያበቃው አለመሆኑን ቢረዱም መንገመ ሪያ እርሱ የጠሩን ርዳታ ይዞ ሄዶ የሹመቱን ደረጃ በመቅመስ ይመሥርትና በሚ ቀጥለው ጊዜ ከርሱ የተሻለ ሰው እንልካለን በሚል መንፈስ የቤርሙዴዝን ጥያቄ ተቀብለው የጦሩን ርዳታ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ፈቅደው ይሆናል ።

በዚህ የተነሣ ከሊስቦን ወደ ሕንድ ሄዶ ከሕንድ ከክርስቶፎሮስ ዶጋማ ጋር ወደ ምጥዋ በመጣበትና በውጊያው ጊዜ ሁሉ ፖርቱጋሎቹ ጳጳስ እያሉ ይጠሩት እንደነበሩ በካስታንሆዞ መጽሐፍ ላይ ተገንዝበናል ።

በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. በየካቲት ወር ፖርቱጋሎቹ ምጥዋ ደርሰው የአርኪቆን ወደብ ይብድበው የኑሮን ጭንቅላት ቆርጠው ለንግሥት ሰብለ ወንጌል የማሸነፋ ቸውን የመገመሪያውን የድል ወሬ እንዲያመለክት ሲልኩ ፣ ከዚያ እንዳነበብነው ሁሉ በደባርዋ ከተማ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ተገናኝተው ባመቱ በ፲፭፻፴፬

(1) በእስክንድርያ ከተዋሕዶው ፓትሪያርክ ሌላ የሮም ጳጳስ የሚሾመው ፓትሪያርክ አለ ።
(2)Hist. de l'abissinie-Jones-E Monroe ገጽ 119

ዓ. ም፡ በየካቲት በአምባ ሠነይት ከግራኝ ጦር ጋር በዚሁ ዓመት በመጋቢት በስሀ ርት ከራሱ ከግራኝ ጋር ተዋግተው ባሸነፉበት ሰዓት ተመልሰው በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. በመስከረም መገባደጃ ላይ በወፍላ ተዋግተው እስኪሸነፉ ድረስ ዮሐንስ በር ሙዴዝ የጵጵስናውን ጉዳይና ኢትዮጵያም ካቶሊክነትን ትቀበል ብሎ ገና ክርክር አላነሣም ነበር ። ያላነሣበትም ምክንያት ንግሥት ሰብለ ወንጌል ሴት በመሆናቸ ውና የንጉሥነት ሥልጣን ስለሌላቸው ወይም እርሱ ጳጳስ ነኝ እያለ የጵጵስና ተግ ባር በተለይ በፖርቱጋሎቹ ዘንድ ሲፈጽም ምንም ቡቱቱ ተቃውሞ አላሳዩም ይሆ ናል ።

ስለዚህ ከንጉሡ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር እስኪገናኝ ድረስ ለውጊያው ዕንቅ ፋት ሳይሆን ጦርነቱ በሚያስፈራበት ሰዓት ከንግሥት ሰብለ ጋር ሆኖ በቅድሚያ እየሸሸ በማያስፈራበት ሰዓት ደግሞ ወታደሩን እያበረታታ እያዋጋ ቆይቷል ።

በዚህ ምክንያት በወፍላ ተሸንፈው ክርስቶፎሮስ ደጋማ ተማርኮ እርሱና ንግ ሥቲቱ ከጦርነቱ ላይ በቅድሚያ ሸሽተው የተረፉትም ፖርቱጋሎችና ኢትዮጵያ ውያን ወደ ስሜን በሽሽት ከደረሱና በዚሁ ዓመት ካፄ ገላውዴዎስ ጋር በሸዋዳ ከተ ገናኙ በኋላ ቤርሙዴዝ ራሱ በጻፈው ራፖር ላይ እንደሚተርከው የፖርቱጋሎቹ ሹማምንትና ዋናውን ሹም አልፎስን ካልዴይራን ሌሎቹንም ከፍ ከፍ ያሉትን ወደ ድንኳኑ በመጥራት «ደባርዋ በነበርንበት ሰዓት በአያችሁት የቤተ ክህነት ስነ ሥርዓትና ልማድ ከኛ ከሮማ ቤተ ክርስቲያን ልማድ ልዩነቱን በማየት ቅር እንዳላ ችሁ አውቃለሁ ። ይኸን የመሰለ ትልቅ አገር የቆየ ልማዱን ባንድ ጊዜ ለመተው አይችልም . . . . . . . . አሁን ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ንጉሡን ለሮማ ቤተ ክርስቲ ያን እንዲታዘዝ ማድረግ ነው ። ይህ የመገመሪያው ዓይነተኛ ተግባራችን ነው ። እርሱም ካቶሊክነትን ተቀብሎ ለሮማ ቤተ ክርስተያን ታዛዥነቱን ሲገልጽ ያገሩ ጌታ ከመሆኑ የተነሣ ሕዝቡ ሁሉ ይከተለዋል» በሚል አነጋገር ወገኖቹን ለራሱ ምኞት እንደሳባቸው ያመለክታል ።

ISIC

በዚህ አነጋገር ፖርቱጋሎቹን ከአግባባ በኋላ ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ ድንኳን ይሄዳል ። በዚያም እናትዮዋ ባሉበት «በአሁኑ ሰዓት በሰማይ የእግዚአብሔርን ክብር በመቀበል የሚደሰቱት ንጉሡ አባትዎ(1) ከትንሽ ዓመታት በፊት ወደ ሮማ ሄጄ የኔ ንም የራሳቸውንም ታዛዥነት ለሊቀ ጳጳሱ እንድገልጽ ልከውኝ እንደነበረ ያውቃሉ። በልጅነትዎ ምክንያት ያን ጊዜ የሆነውን አያስታውሱ እንደሆነ ራሳቸው በእጃቸው ፈርመው ለሮማው ሊቀ ጳጳሳት መተማመኛ የሰጡኝ ደብዳቤ እነሆ ይኸውና ደብ ዳቤውም አባትዎ የሮማ ሊቀ ጳጳስ የሊቀ ሐዋርያት የጴጥሮስ ተከታይ መሆኑንና የዓለም ቤተ ክርስቲያን አለቃ መሆኑን ያመኑበትን አስረጂ ነው ። ስለዚህ እርስዎ በአባትዎ እግር ከነገሡ ዘንድ ይኸንኑ የአባትዎን ውሳኔ በመከተል ለሮማ ሊቀ ጳጳሳት ታዛዥነትዎን መግለጽ ግዴታ ነው ። ይኸንንም ሲያደርጉ የእግዚአብሔ

(1) ዓፄ ልብነ ድንግልን ማለቱ ነው ። ክብር የሚቀበለው የሚለው መንግሥተ ሰማያት የገባው ለማለት ነው ።

ርን ትእዛዝ መፈጸምዎ ስለሆነ የፖርቱጋልን ንጉሥና የወንድሞቹን የሌሎቹን ነገሥታት ወንድምነት አግኝተው ከነርሱ የሚያስፈልግዎን ርዳታ ያገኛሉ» ብሎ እንደነገራቸው ይገልጻል (1) ።

በዚህ ጊዜ ያለውን የዓፄ ገላውዴዎስን ችግር ለመረዳት ቀላል ነው ። ከአብ ርሃ ወአጽብሐ ጊዜ (፬ኛ መቶ ዓ.ም.) እስከ እዚህ ጊዜ ድረስ ፩ሺ፩፻ ዓመት ጸንቶ የቆየውን የተዋሕዶ ሃይማኖት ለውጠው ካያት ከቅድም አያት ዠምሮ በኢትዮጵ ያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሲሰደብ ሲነቀፍ የነበረውን የካቶሊክ ሃይማ ኖት ተቀብለው የሮማ ጳጳስ ታዛዥ ለመሆን የማይዋጥ መራራ ጉርሻ ይሆንባቸ ዋል ። እርሳቸውስ የጊዜውን ችግር አይተው ቢቀበሉ ሕዝቡና ካህናቱ ይሞታሉ እንጂ መቼ ይቀበላሉ ? ሕዝቡና ካህናቱ የማይቀበለውን እርሳቸው ለብቻቸው አዎን ለሮማ ጳጳስ ታዛዥ ነኝ አማኝ ካቶሊክ ነኝ ቢሉ ጉዳዩ እስከምን ድረስ ሊራ መድ ይችላል ? ቤርሙዴዝ ለፖርቱጋሎቹ ንጉሡን በካቶሊክ ማሳመን የመዠመ ሪያ ተግባራችን ነው እርሱ ሲያምን ሕዝቡ ይከተለዋል ያለው በሙሉ ሊታመን አይችልም ። ምናልባት ለጊዜው የጦርነቱ ችግር የግራኝ እሠቃይነት የመረረ ቸው መከራና ስደት የሰለቻቸው ወይም በጠባያቸው ለሁሉም ግዴለሽነት ያላ ቸው ይቀበሉት ይሆናል ። ነገር ግን በነርሱ አንጻር ያለው ሃይማኖት እጥባቂ የሆ ነው ደግሞ ሕዝቡም ካህናቱም ይኸን ከመቀበል በእግዚአብሔር ትእዛዝ የመጣ ውን መከራ በትዕግሥት መቀበል ይሻላል ሳ[illegible]አይቀርም ።

ያባትዎን ታዛዥ መሆን እርስዎ በልጅነትዎ ምክንያት አያስታውሱት እንደ ሆን በእጃቸው የተፈረመውን የጽሑፍ ሰነድ ይኸውና ብዬ አሳየሁዋቸው ብሎ በጽሑፉ ያሰፈረውን ይኸን ሰነድ ማንም ሊያገኘው አልቻለምና ስለርሱ ሐተታ መስጠት ችግር ነው ። ነገር ግን ከይኵኖ አምላክ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ያሉ ነገሥ ታት ባይሆን ማኅተማቸውን ያትማሉ እንጂ በተለይ በዚህ በ፲፫ኛ መቶ ዓመት ያሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት እንደሠለጠኑት አገሮች ነገሥታት በደብዳቤና በማና ቸውም ሰነድ ላይ በእጃቸውና በስማቸው ፊርማ ሊፈርሙ አይችሉም ። ጽሕፈት የማያውቁ ሆኖ አይደለም ነገር ግን የተለመደ አይደለም ። ለሮማ ሊቀ ጳጳሳት የጻ ፉት ደብዳቤስ እንደሆን ለጳጳሱ ሳይሰጥ እንደምን መልሶ አመጣው ።

የሆነ ሆኖ ዓፄ ገላውዴዎስ ከቤርሙዴዝ አንደበት ይኸን ንግግር ሲሰሙ ወዲያው መልሰው አንተ አባቴም ጳጳሴም አይደለህም ። አንተ የፈረንጆቹ ጳጳስ ነህ እንዲያውም በአራት አማልክት የምታመልክ አርያን ነህ ለወደፊቱ አባቴ ብዬ አልጠራህም ፤ ብለው ድርቅ ያለ መልስ ሲሰጡት ውሸትዎ ነው እኔ አርያን አይደ ለሁም (2) ። አራት አማልክትም አላመልክ ብሎ ለሮማ ጳጳስ አልታዘዝም በማለ

(1) Hist. du christianisme - La Croze. ገጽ 153 - 156

(2) አርያን በኒቅያ ጉባኤ የተወገዘውን የአርዮስን ትምህርት የሚከተል ማለት ነው ።

ታቸው ደግሞ ገዘታቸው (1) እርሳቸውም የተገዘትህና የተረገምህ አንተ ነህ ብለው ትተቆጥቶ ትቷቸው ወደ ፖርቱጋሎቹ ሄደ ። ለነርሱም በርሱና በንጉሡ መካከል የሆነውን ሁሉ ተርኮ ሲጨርስ «ንጉሡ ለሮማ ቤተ ክርስቲያን አልታዘዝም ብሎ እንደ ንስጥሮስ እንደ ዲዮስቆሮስ በመናፍቅነቱ ስለጸና ከፖርቱጋል ንጉሥና ከሮማ ሊቀ ጳጳስ በተሰጠኝ ሥልጣን በማናቸውም ረገድ ለንጉሡ እንዳትታዘዙ ምንም ዓይነት ርዳታ እንዳታደርጉ አዝዣችኋለሁ ። ይኽን ትእዛዜን የተላለፈ ተወግዞ በሞት ይቀጣል« አላቸው (2) ።

በዚህ ዓይነት የቤርሙዴዝ የጌቶቹ የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማ ጳጳስ ማስፈራሪያ እነዚሁ ለርዳታ የተላኩት የፖርቱጊዝ ወታደሮች ናቸው ። እነርሱም በተለይ ራሱ ቤርሙዴዝ በዚህ ወታደሮች ርዳታ ዋጋ የኢትዮጵያን ተዋሕዶነት በካቶሊክነት ሊገበይ አጥብቆ ፈልጓል ። በዚያ ሁሉ ፍቅርና የመተሳሰብ መንፈስ በዚያ ሁሉ ጦርነትና ልቅሶ መካከል ዋናው ጠላት ግራኝ አህመድ ከመውደቁ በፊት ቤርሙዴዝ የራሱን የሥልጣንና የሃይማኖት ምኞት ለመፈጸም ይኽን ጥያቄ የደነቀረው ንጉሡም ንግሥቲቱም ምንም ሌላ መውጫ ስለሌላቸው ያለ ፖርቱጋሎቹም ርዳታ ግራኝን ስለማያሸንፉ በግዳቸው የኔን ጥያቄ ይቀበላሉ በሚል መንፈስ ነው ። በእርግጥም ግምቱ የተሳሳተ ሊሆን አይችልም ። ፲፭ ዓመት ሙሉ ክርስቲያኖቹውን ሕዝብ ማርኮ በሥቃይ የገደለው ግራኝ አህመድ ጥይትና ጠበንጃ በያዘ ወታደር ካልሆነ በቀር በምንም ሊወድቅ እንደማይችል የታወቀ ነው ። ይኽንንም ጥያቄ ያቀረበው ግራኝ ከወደቀ በኋላ መቼም በጅ አይሉም በማለት ከግራኝ ጋር በደንቀዝ (በዘንተራ) ጦርነቱ ከመደረጉ በፊት በሸዋዳ በነበሩበት ሰዓት ነው ።

ISIC

ስለዚህ በዚህ በሁለቱ ወጥመዶች ውስጥ ወጣቱ ዓጼ ገላውዴዎስና እናታቸው ንግሥት ሰብለ ወንጌል ገብተው እንደተቸገሩ ይታያል ። ነገር ግን ከሁለቱ ወጥመድ ለመውጣት በእውነትም በዚያን ሰዓት እናትና ልጁ በጣም ማሰብ አለባቸው ። ከሁለቱ ወጥመድ ወይም ከሁለቱ ነገሮች አንደኛውን መምረጥ ግዴታ ስለሆነ ለጊዜው የርሱን ጥያቄ ተቀብሎ ግራኝን መጣልና ከዚያ ወዲያ የሚሆነው ይሆናል በሚል ውሳኔ ከርሱ ጋር ለጊዜው መስማማትን መረጡ ። ማንም መሪ በነርሱ ሥፍራ ቢሆን ከዚህ የተሻለ ምርጫ በእንደዚህ ያለ አስቸጋሪ ጊዜ ሊያገኝ አይችልም ። የስምምነቱን ሁኔታ በሚቀጥለው ምዕራፍ እናንብብ።

(1) እርዮስም ወልድ ፍጡር እለ እንጂ አራት አማልክት አላለም ። ነገር ግን ንስጥሮስ የአምላክ ልጅና የማርያም ልጅ ብሎ ከሁለት ስለከፈለው እንግዲያው ከመንፈስ ቅዱስና ከአብ ጋር አራት አማልክት ማድረግህ ነው ተብሎ ተነቅፏል ። ካቶሊኮቹም ሁለት ባሕርይ ስለሚሉ እርሱን መጠጋታቸው ነው ተብሎ አራት አምላክ አምላኪዎች ተብለው ታምተዋል ። መዝገበ ሃይማኖት SCRIT. TEOLOGICI በሚል እርእስት ቼሩሊ ያሳተመው ገጽ 8 - 10 ተመልከት ።

(2) ዲዮስቆሮስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ በ፩ ባሕርይና በ፪ ባሕርይ ምክንያት በኤፌሶን ተከራክሮ ከረታ በኋላ ቀጥሎ በኬልቄዶን ጉባዔ ተረታህ ተብሎ ተደብድቦ የታሠረ ነው ።

## ምዕራፍ ፻፴፯

### ያፄ ገላውዴዎስና የቤርሙዴዝ ወደ ስምምነት መቅረብ — ዓፄ ገላውዴዎስ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለጳውሎስ ፫ኛ የጻፉት ደብዳቤ (፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ኅዳር - ጥር)

ዮሐንስ ቤርሙዴዝ በዚህ ባነበብነው ዓይነት ፖርቱጊዞቹ ለንጉሡ ለዓፄ ገላውዴዎስ በማናቸውም ረገድ እንዳይታዘዙ ባደረገ ጊዜ በንጉሡ በኩል እነዚህን ወታደሮች ከቤርሙዴዝ ለይቶ ወደርሳቸው ለመሳብ ሙከራ ሳይደረግ አልቀረም ። ወታደሮቹ በርሱ ትእዛዝና ግዝት ሳይታሠሩ እርሱን ትተው ወደርሳቸው ቢደረቡ ትልቅ የመውጫ መንገድ ተገኘ ነበር ። ስለዚህ ቤርሙዴዝ ከርሳቸው ድንኳን በቁጣ ወጥቶ ከፖርቱጋሎቹ ጋር ተገናኝቶ የሆነውን ተርኮ ለንጉሡ ሁለተኛ እንዳይታዘዙ ሲያስጠነቅቅ ይኸን የትእዛዝ ማስጠንቀቂያ ሁሉም ይቀበሉት ወይም እነ ካስታንሆዞ እነአርያስ ዲያዝ ንጉሡ እውነት አላቸው ብለው ከርሱ ይለዩ አይለዩ ለጊዜው አናውቅም ።

ካስታንሆዞ በዚያ ሁሉ የጦርነት ታሪኩ ላይ እንደምናስታውሰው የንጉሡን ደግነትና ፍቅር እየዘረዘረ ሲጽፍ የዚህን የቤርሙዴዝን ሃይማኖታዊ ጥያቄና ጠብ በፍጹም አያነሣውም ። ምናልባት የቤርሙዴዝን አሳብ ከልቡ ስላልተቀበለው ይሁን ወይም ገላውዴዎስን ደግፎ ባገሩ ሕዝብ ዘንድ የከዳተኝነት ትርጉም እንዳያስከትልበት ይሁን የዚህን ዓይነተኛ የሃይማኖት ጉዳይ ወዳገሩ ተመልሶ በጻፈው በዚህ ታሪካዊ መጽሐፉ ላይ ከማንኛውም ምዕራፍ ላይ ሊጠቅሰው አልፈለገም ።

ቤርሙዴዝ ከርሳቸው ዘንድ ተቆጥቶ ወጥቶ ከሄደና ከፖርቱጋሎቹ ተነጋግሮ ትንሽ ጊዜ እንደቆየ ዓፄ ገላውዴዎስ ፫ሺ ወቄት ወርቅ አሲዘው ከሹማምንቶቻቸው አንዱን ወደ ፖርቱጋሎቹ ልከው ከአለቃቸው ጋር ይኸን ወርቅ እንዲከፋፈሉ በዚህ በጦርነት ሰዓት ትተዋቸው እንዳይሄዱና ከጠላታቸው በሚዋጉበት ጊዜ እንዲረዱዋቸው መልእክት መላካቸውንና እነርሱም ስጦታቸውን ለመቀበል በርሳቸውና በቤርሙዴዝ መካከል ያለው ጠብ እንደሚያግዳቸው የጠየቁትንም የርዳታ ጥያቄ እንደማይፈጽሙ መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጣል ።

ከዚሁ አያይዞ ወታደሮቹ ወርቁንም አንቀበልም ፈቃድዎንም አንፈጽምም የሚል መልስ ከሰጡ ወዲህ ባፄ ገላውዴዎስ ዘንድ ምክር መያዙን በምክር እናትዮዋ ከሹማምንቱና እርሱ ከቀባው ሊቀ ጳጳስ ጋር (1) ወደ ድንኳኑ መጥተው ይቅርታ እንዲጠይቁትና እንደጠየቀው ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ታዛዥነታቸውን ለማረጋገጥ መወሰናቸውን ያመለክታል ።

(1) እዚህ ላይ ፈረንሳዊው "Archevêque" ያለው ትርጓሜው ሊቀ ጳጳስ ነው ። ነገር ግን እርሱ ከሊቀ ጳጳስ በታች ጳጳስ ሆኖ እንዴት በዚህ ሹመት ሊሳውን ይቀባል ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ራሱን "Patriarche" እያለ ስለሚጠራ በዚሁ መሠረት በዚህ ማዕርግ ለመሾም ችሎ እንደሆን አይታወ ቅም ምናልባት ቆሞስ ፣ ወይም ኢጲስ ቆጶስ ብሎ ሾሞ ይሆናል ።


ስለዚህ ንግሥቲቱ ወደ ድንኳኔ መጥተው «አባክህ ስለ ቅድስት ማርያም ስትል ወደ ልጇ ወደ ንጉሡ አብረን እንሂድና ይቅርታ ጠይቀህ ያልኸውን ሁሉ ይፈጸምልሀ» ብለው ለመኑኝ ። እኔም «እነዚህን ልጆቼንና ጓደኞቼን ይገፍ ወደ አገሬ ከመመለስ በቀር ወደ ንጉሡ ለመሄድ አንድም እርምጃ አልራመድም» የሚል መልስ ሰጠሁ ። በዚያን ጊዜ ንግሥቲቱ በፊቴ ተንበርክከው እያለቀሱ «በእግዚአብሔር ፊት ይገፍሃለሁ ወደ ንጉሡ ሂድና የምትለውን ሁሉ ይፈጽም ልሀ« ብለው አጥብቀው ስለለመኑኝ ዕንባቸው አሳዝኖኝ እሺ ብዬ ተነሥቼ ከንግሥ ቲቱ ጋር ወደ ንጉሡ ድንኳን አብረን ሄድን ንጉሡም ከድንኳናቸው ወጥተው በት ሕትና እጄን ስመው በአደረጉት ነገር ይቅርታ ጠየቁኝ ። ከዚያ ሦስታችንም ከመ ሬት ተቀምጠን ንጉሡ ንግግር ዠምረው «መልካም ነው ለሮማው ሊቀ ጳጳስ መታ ዘዝ ደስ ይለኛል ። ለዚህም መታዘዝ አባቴ ከዚህ በፊት የሰጡት ቃል ይበቃል» ቢሉኝ የለም አዲስ ንጉሥ ሲነግሥ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ እስከ አለበት ድረስ የታዛዥነ ቱን መልእክት መላክ ባገራችን (በአውሮፓ) ልማድ ስለሆነ ከዚህ በፊት እንደአባ ትዎ አልላኩምና ራስዎ ጽፈው ለመቀበል ሥልጣን በተቀበልሁት በኔ እጅ ሊልኩ ይገባል ። እንደዚሁም በምድር የክርስቶስ እንደራሴ ከሮማ ጳጳስ በቀር ሌላ የለም በምድርም ካንዲት የሮማ ቤተ ክርስቲያን በቀር ሌላ የለም ብለው በራስዎ ፊር ማና ማኅተም አረጋግጠው ይኸው ቃልዎ ባንድ ባለሥልጣን እንደበት በአዋጅ ለአገርዎ ሕዝብ ይታወ[illegible]ዬአቸው እሺ ብለው አዋጁ በነጋሪትና በጥሩምባ በዓል ተደርጎ ታወጀ ይላል (1) ።

በዚህ ዓይነት ላዬ ገላውዴዎስ የፖርቱጋሎቹ ርዳታ ምርቅ ያለበት ፍት ፍት ሆኖባቸዋል ማለት ነው ። የሆነ ሆኖ በዚህ ጊዜ ከሁለት ክፉ አንዱን ለመም ረጥ ግዴታቸው ሆነ እንዳልነው ከአባታቸው ጋር በልጅነት ወራት በመከራና በስ ደት የኖሩት ወጣቱ ገላውዴዎስ ከክርስቲያን አገር የኔንም የአባቴንም ቁጭት የሚወጣ ርዳታ መጣልኝ ብለው ሲደሰቱ ገና ግራኝ በሕይወት እያለ ይህ ኃይለኛ ጠላት ወደፊት ምን እንደሚያደርግ ሳይታወቅ ከወዳጅ አገር የመጣው ወዲህም የርሳቸው የክርስትና አባት ነኝ የሚለው ቤርሙዴዝ በወታደሮቹ ጉልበትና በያ ዙት መሣሪያ ብቻ በመመካት የርሳቸውን ውድቀትና ለብቻ ግራኝን ሊመክቱ አለ መቻላቸውን በመገመት ይኸን የመሰለ እርሳቸውም ጠቅላላውም ሕዝብ የማይቀ በለውን የሃይማኖት ለውጥ ጥያቄ አመጣባቸው ።

በዚህ ችግር ፊት ንጉሡ የእርሱን ጥያቄ እምቢ ብለው እርሱ ከነወታደሩ ከነ መሣሪያው ከተመለሰ በኋላ የሕዝቡ መከራ በግራኝ ወራሪነት ከሚቀጥል ብለው ለጊዜው ፈቃዱን ለመፈጸም እሺ ብለው እውጀዋል ማለት ነው ።

በዚህ ምክንያት በዚሁ ጊዜ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ አንድ ደብዳቤ ጻፉ ። ፓሪስ የነበ ርሁ ጊዜ አንዳንድ የታሪክ ሰነድ ፍለጋ ወደ ሮማ እንደ አው. ቀ. ፲፬፻፶፮ ዓ. ም. ሄጄ ሳለ በሮማ የቫቲካኑ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ( VAT Etiop )ቊጥር 75 ተሰ

(1) Hist. du Christianisme- La Croze ገጽ 158 - 160


Meyer gekauft in Firenze 1103

Bibliothecae Vaticanae dedit Willy Meyer Spireus 1904

ቂ፡መልእክት፡እም፡ኀበ፡ንጉሥ፡አጽናፍ
ሰገድ፡ገላውዴዎስ፡ትብፃሕ፡ኀበ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡መንበረ፡ጴጥሮስ፡ክብሮት፡
ዘህላውክ፡አጽውሎስ፡አቡነ።
ሰላም፡ለከ፡ሰላመ፡ሠለሰ፡የሀሉ፡ምስሌከ፡አመነ፡
ሰማዕኬ፡ዘወሀብከነ፡አቡነ፡ዮሐንስ፡ክሬዘብ፡
እንበርና፡ውስተ፡መንበረ፡ጳጳስና፡ወሊተሂ፡
በርከኒ፡አበ፡በረከት፡አብ፡ለውሉድ፡ብክዑብ፡
ወበከመ፡ባረከ፡አብርሃም፡ለይስሐቅ፡ወይስሐቅ
ለያዕቆብ፡ወቡሩኪ፡ለመኑ፡ጀንግል፡ሞተ፡
እኑዮ፡ሚናስ፡አሐዝዎ፡ተንበለተ፡ለነስ፡
መስሌነ፡በከመ፡ይቤ፲ወንጌል፡ብፁዓን፡
ለ፡ይስደዱ፡በእንተ፡ጽድቅ፡እስመ፡ሎሙ፡
ይእቲ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ሰማዕኩ፡እአቡነ፡
ጳውሎስ፡ሊቀ፡ጳጳስነ፡ዘሮማ፡ዘትቀኒ፡፲
ነገሥት፡ክርስቲያን፡ይረስዑ፡አበደም፡
ደም፡ንሕነሰ፡ክርስቲያን፡ሊተረእኑ፡
ዘይነዕውኒ፡ወዓረብ፡ንሕነሰ፡ተመሰልነ፡
ከመ፡አባግዕ፡ፈንዎሙ፡በበሃሬ፡ለቀትል፡
ጸርነ፡እምይእዜሰ፡በጽሑ፡ሠሀበ፡እግዚእ
ብሔር፡ኀቤነ፡በከመ፡ተሠሀሎሙ፡ለእስራኤል
ለመ፡ወጻእ፡እምግብጽ፡ወአኅለፎሙ፡በሐር
በእግር፡ወአስጠምዎ፡ለፈርዖን፡ውስተ፡በሐር፡

የመዠመሪያዪቱ (ኦርጅናል) ያፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤ ለሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስለዮሐንስ በርሙዴዝ የጻፉት የመዠመሪያው ገጽ ። (ከቫቲካን ቤተ መጻሕፍት 75 ቍጥር ላይ የተገኘ)

ጥቶት ከሌሎች ሰነዶች ጋር የተቀመጠ ከኘሁ ከዓፄ ገላውዴዎስ ለሮማው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለጳውሎስ ፫ኛ የጻፉትን ደብዳቤ አገኘሁ ። ይህቺም ደብዳቤ ቤርሙዴዝ ይኸንኑ ጥያቄ በጠየቀበት ሰዓት ግራኝ ከመሞቱ በፊት ስለርሱው ሹመት የተጻፈች መሆኗ በላይዋ ላይ ንጉሡ ወይም ጸሐፊያቸው ያሠፈሩዋቸው ቃሎች ያስታውቃሉ ።

ደብዳቤው የተጻፈው ባልተቋቋመ መንግሥት በደህና ጸሐፊ እጦት ምክንያት ይሁን ወይም ልብ ያልፈቀደውን ከመጻፍ የተነሣ ይሁን በደብዳቤው ላይ ብዙ የፊደል ግድፈት ከመኖሩ በቀር ብርዑ ራሱ ለካስታንሆዞ እንደጻፉት ዓይነት አያምርም ።

ስሕተት የመሰለኝን ቍጥር እየሰጠሁ እርማቱን በግርጌ አድርጌዋለሁና የደብዳቤውን ቃል እንመልከት ።

«ፈናዌ መልእክት እምኀበ ንጉሥ አጽናፈ (1) ሰገድ ገላውዴ (2) ዮስ ትብፃሕ (3) ኀበ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮማ መንበረ ጴጥሮስ ክብርት ዘሀለውከ እ ጳውሎስ አቡነ ።

ሰላም ለከ ሰላመ ሥላሴ የሀሉ ምስሌከ እሜን ስማዕኪ (4) ዘወሀብከነ አቡነ ዮሐንስ ከሪዘከ (5) አንበርናሆ ውስተ መንበረ ጵጵስና (6) ወሊተሂ ባርኩኒ አባ በረከተ እብ ለውሉድ ብከዑከ (7) ወከመ ባረኮ አብርሃም ለይስሐቅ ወይስሐቅ ለያዕቆብ ወቡየሂ ልምነ (8) ጸጋሃግል ሞተ ወእኅየ ሚናስ አሐዝዎ ተንባላተ (9) ለነሰ ተመሰልነ በከመ ይቤ ወንጌል ብፁዓን እለ ይሰደዱ በእንተ ጽድቅ እስመ ሎሙ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት ስማዕኒ እ አቡነ ጳውሎስ ሊቀ ጳጳስነ ዘሮሜ ዘትቀኒ ፯ ነገሥታት ክርስትያን (10) ይረስዕኑ እበ ደም ደሞ ንሕነሰ ክርስቶሳውያን ኢትሬትኑ (11) ዘይነዕውነ (12) ተኳል ወዓረብ ንሕነሰ ተመሰልነ ከመ እባግዕ ፈንዎሙ በበሀገሩ ለቀትለ ጸርነ እም ይእዜሰ በጽሐ ሣህለ እግዚአብሔር ኀቤነ በከመ ተሣሃሎሙ ለእስራኤል እመ ወጽኡ እምግጽ (13) ወእኅለፎሙ ባሕር በእግር ወእሰጠሞ ለፈርዖን ውስተ ባሕር ምስለ ኩሉ ሠራዊቱ ወካዕበ ኢ.ስማዕከኑ ኢያሱ ወልደ

(1) ፍ
(2) ድ
(3) ጸ
(4) ኩ
(5) ዮሐንስ ቤርሙዴዝ
(6) ጥንት የጸ ተ ጸ ደ የመሳሰሉት የሳድስ ቅጥል ከግራ ነበር
(7) አይገባኝም
(8) አቡየሂ ልብነ ድንግል
(9) ተንባላት
(10) ክርስቲያን
(11) ኢትሬእይኑ
(12) ዘይነዕውነ
(13) ግብጽ

ነዌ ዘሞአሙ ለጁቱ ነገሥተ ከናዓን (1) አቂሞ ፀሐየ በገባኦን ወርኀኒ በቈላተ ኤላ ወበጸሎቱ ለሆሜዕ ወከማሁ አትነ (2) ጽሌ (3) ከመ ልማድከ (4) ይሰምዓከ እምላከሙ ለክርስቲያን ወፈኑ ሠራዊተከ ቦ በምራቅ (5) ወቦ በምዕራብ ወቦ በሰሜን ወቦ በደቡብ ቅንኡ ለእንተ ተዓቢ ጸገ (6) በከመ ይቤ መጽሐፍ እምላከ ሰላም የሀሉ ምስሌከ አሜን ። ዘለአከነ (7) ገላውዴዎስ ሀንተ (8) ለዝ ጴጥሮስ ስምዕዎ ዘተናረ (9) ንሕነሰ ኮነ ሐደ (10) ሥጋ ወ፩ መንፈስ» ።

የደብዳቤው ትርጓሜ በግልጽ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ። «የተላከ ከን ጉሥ አጽናፍ ሰገድ ገላውዴዎስ ይድረስ በከበረችው በሮማ የጴጥሮስ ወንበር ለተ ቀመጥሽው አባታችን የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ። ሰላም ላንተ ይሁንልህ የሥላሴም ሰላም ካንተ ጋር ይሁን አቡነ ዮሐንስ ከሪዘከን እንደሰጠኸን ስለሰማን በመንበረ ጵጵስና አስቀምጠነዋል ። አባት ልጁን እንደሚባርከው አብርሃም ይስሐቅ ይስ ሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው እኔንም ባርከኝ ። አባቱ ልብነ ድንግል ሞተ ወንድ ሜን ሚናስን እስላሞች ማረኩት እኛም እንደተበተን (በጐች) መሰልን (11) ወን ጌል ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ የተመሰገኑ ናቸው መንግሥተ ሰማያት የነርሱ ናትና እንዳለው (12) ሊቀ ጳጳሳት አባታችን ሆይ ሰባት የክርስቲያን ነገሥታት እንደምት ገዛ ሰማሁ ። የአባት ደም . . . . . ይረሳልን (13) ዓረብና ቱርክ ? እንደሚያሳድዱን አታይምን እኛ እንደ በግ መሰለናል ። በየአገሩ ጠላቶቻችንን ለመውጋት ላካ ቸው (14) ፈርዖንን ከነሠራዊቱ አስጥሞ እስራኤልን ከግብፅ በእግር ባሕርን አሻ ግሮ እንዳዳናቸው ለኛም አሁን የይቅርታው ፲፱፻ ደረሰልን ። ደግሞስ ኢያሱ የነዌ ልጅ በከነዓን ሰባቱን ነገሥታት ፤ በገባዖን ፀሐይን ፤ በኤላ ምድረ በዳ ጨረቃን አቁሞ እንዳሸነፋቸው አታውቅምን (15) በሆሴዕ ጸሎት እንደዳኑ (16) አንተም የክርስቲያን አምላክ ጸሎትህን ይሰማልና ጸልይ ። ሠራዊትህን በምሥራቅም በምዕራብም በሰሜንም በደቡብም ላክ መጽሐፍ ለምትበልጠው ጺጋ ቅኑ እንዳለ

(1) ነገሥተ ከነዓን
(2) አንተኒ
(3) ጸሊ
(4) ልማድከ
(5) ምሥራቅ
(6) ጺጋ
(7) ዘለአከዎ አነ
(8) ሀየንተ
(9) ዘተናገረ
(10) አሐደ
(11) የተበተኑ በጎች የሚለው ቃል ሳይጐድለው አይቀርም ። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቍ. 12
(12) የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቍጥር 10
(13) የጐደለ ቃል ያለ ይመስላል ወይም ልጁ የአባቱን ደም ይረሳልን ማለታቸው ይሆናል ።
(14) ወታደሮች የሚል ቃል ጐድሏል
(15) ኢያሱ ወልደ ነዌ 10 ቍ. 12
(16) ትንቢተ ሆሴዕ ምዕራፍ 11 - 12

የአምላክ ሰላም ካንተ ጋር ይሁን (1) እኔ ገላውዴዎስ ስለ ቃሌ (2) አድርጌ የላክ ሁትን ኤጥርስን ስማው እኛ አንድ ሥጋ አንድ መንፈስ ሆነናልና» ።

እነሆ በደብዳቤው ላይ ዮሐንስ ክሪዘክ የሚሉት በፖርቱጋልኛ ( JOAO BERMUDEZ በፈረንሳዊኛ (Jean Bermudez) የሚባለውን እርሳቸው በኢትዮ ጵያዊ አጻጻፍ ዮሐንስ ብለውታል ፤ ነገር ግን ክሪዘክ የሚለው ቃል ከቤርሙዴዝ መራቁ ያው ያጻጻፍ ጉድለት መሆን አለበት ።

በደብዳቤያቸው መጀመሪያ ላይ "ዮሐንስን እንደሰጠኸን ስለሰማሁ በጵጵ ስናው ወንበር ላይ አስቀመጥነው ያሉት ይህ ሰው ከሮማ ሊቀ ጳጳስ የተሾመበት ምንም ዓይነት ሰነድ ሳያቀርብላቸው በቃሉ ብቻ ተሾሚያለሁና ሹመቴን ያጽድቁ ልኝ አለዚያ ያመጣሁትን ወታደር ይዤ እመለሳለሁ ብሎ ስለ አፋጠጠ በጵጵስ ናው ወንበር ላይ ማስቀመጣቸውን ገልጸዋል (3) ። መቼም እውነቱን ለመከተል እንጂ እርሱ ከሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የተሾመበት ማስረጃ ቢኖርም ባይኖርም ዋጋ የለውም ። እርሱን ለመሾም ወይም ሾመናል ብሎ ለመጻፍ ግዴታ ያመጣ «ሹሙኝ ያለዚያ የፖርቱጋሎቹን ወታደሮች ይዤ እመለሳለሁ» ያለው ማስፈራ ሪያ ብቻ ነው ። በዚያ የችግርና የመከራ ሰዓት ለአገሩ ሕዝብ የሚያስብ ማናቸ ውም ንጉሥ ይኸን ርላቸው የወሰዱትን እርምጃ ሊያደርገው የሚችል ነው ።

ደብዳቤውን የጻፉበት ሰዓት ከግራኝ ሞት በፊት ከወፍላው ጦርነት በኋላ ከፖርቱጋሎቹ ጋር በሰሜን በተለይ በሸዋዳ ከተገናኙ ወዲህ መሆኑ "አባቴ ልብነ ድንግል ሞተ ወንድሜ ሚናስ ተማረከ አሁን ግን የእግዚአብሔር የይቅርታው ቀን ደረሰ የሚለው አጻጻፋቸው ይገልጻል ። ደብዳቤው አጭር ወይም በችኮላ የተጻፈ ከመሆኑ የተነሣ የሚናስን ምርኮ ያባታቸውን ሞት ሲገልጡ የወንድማቸውን የፊ ቅጦርን ሞት በተለይም ከሁለት ወር በፊት ተማርኮ የሞተውን የክርስቶፎሮስን ሞት አይጠቅሱም ።

በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. በመስከረም ፫ ቀን የወፍላ ጦርነት ሆኖ ደጋማ ከተማረከ በኋላ በወሩ በጥቅምት ከፖርቱጋሎቹና ከእናታቸው ከተገናኙ ወዲህ ክርክሩና ጠቡ የተነሣውም በዚሁ በጥቅምትና በኅዳር ወር ላይ ስለሚሆን ጠቡና ክርክሩ በዚህ ዓይነት በስምምነት ተዘግቶ ግራኝን ለመውጋት በወይና ደጋ በኩል ወደ ደን ቀዝ ጉዞው የተደረገው በየካቲት ወር መጀመሪያ ላይ ስለሆነ ደብዳቤው የተጻፈ በት ዓመት ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ወሩ ታኅሣሥ ወይም ጥር ይሆናል ማለት ነው ።

በደብዳቤያቸው ላይ የሮማን ሊቀ ጳጳስ ጳውሎስን ፯ ነገሥታት የምትገዛ ያሉ ትን ተመልክተናል ። ይኸን የመሳሰለውን ወሬ የሚነግሩዋቸው ባጠገባቸው ያሉት የፖርቱጋል ካቶሊኮች በተለይ ደግሞ ሊቀ ጳጳሱን አክብሮ ለመክበር የሚፈልገው

(1) ጢሞቴዎስ 4 - 14

(2) እንደራሴ ለማለት ነው

(3) ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ከጳውሎስ ፫ኛ የተሰጠኝ ማናቸውም ሰነድ በወፍላ ጦርነት ተዘረፈ ይላል Histoire du christ...... ገጽ 264

ይኸው ቤርሙዴዝ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። አሳባቸውም የሮማን ጳጳስ ሥልጣን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ በማሳየት ዓፄ ገላውዴዎስን ወደዚሁ የታዛዥነት ማኅበር ለማስገባት ነው ።

እነዚህም ሰዎች በአሁኑ ጊዜ የጀርመኑን ንጉሥ ነገሥት በሮማ ጳጳሳት ላይ መሟገን ብዙም ጊዜ የሊቃነ ጳጳሳቱን የነልዮንን የነቀሌምንጦስን አሳብ እየተቃወመ ግዛታቸውን ሮማን እስከ ማዘረፍ መድረሱን ፤ ሀንሪ ፰ኛ የእንግሊዝ ንጉሥ ሁለተኛውን ጋብቻውን ስለተቃወሙት ዋና የሊቃነ ጳጳሳቱ ጠላት ሆኖ በእንግሊዝ አገር የሊቀ ጳጳሱ ወገን ነኝ የሚለውን ሁሉ እያሠረ እየፈታ እስከ መግደል መድረሱን መቼም አይገልጹላቸውም ።

ይሁን እንጂ በማናቸውም ረገድ የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ በተቀበለው በቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ እግር የተቀመጡት የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በመንፈሳዊ አባትነት ቀብቶ የማንገሥ አውግዞና ገዝቶ ከዙፋን የማውረድ ፤ ባርኮ ሚስት የማጋባት ፍቺን አውግዞ የመከልከል ሥልጣን ስለ አላቸው በካቶሊክ ነገሥታት ዘንድ ያላቸው ክብር በጣም ከፍ ያለ ነው ። ክርስቶስ ለጴጥሮስ በምድር ያሠርከው በሰማይ የታሠረ ይሆናል ፤ ብሎ የነገረው ቃል (1) ለነዚህ ለተከታዮቹ የሚጸድቅ ነው ነው ብሎ በማመን አብዛኛ ጊዜ የካቶሊክ አገሮች ነገሥታት በሥጋዊም በመንፈሳዊም ረገድ ከፈቃዳቸው አይወጡም ። እነዚህም የፈረንሳዊ ፣ የፖርቱጋል ፤ የኤስፓኝ ፤ የፖሎኝ የናፖሊና የሲሲሊ መንግሥታት ናቸው ፤ ነገር ግን እነዚህ ሁለቱ የመጨረሻዎቹ የናፖሊና የሲሲሊ በውጭ አገር ያልታወቁ ታናናሽ መንግሥታት ስለሆኑ በነርሱ ፈንታ የጠቡን ጉዳይ ወደ ውጭ በማድረግ የእንግሊዝና የጀርመንን መንግሥታት ጨምረው ፯ ነገሥታት ብለው ነግረዋቸው ይሆናል ።

በዚህ ጊዜ ኤስፓኝ በአንድነት ስለተጠቀለለ ከፊልጶስ ዳግማዊ በፊት በውስጡ የናቫር የካስቲይ ፤ የአራጎን አገሮች ነገሥታት ይነግሡባቸዋል ። ስለዚህ ታላላቆቹ ፯ አይሞሉም ታናናሾቹን ደግሞ የደራረቡዋቸው እንደሆነ ወደ አሥር ይጠጋሉ ። የቀሩት የዛሬዎቹ የቤልጅክ የሆላንድ የዳንማርክ የነምሳ አገሮች ከስዊኑ ኢጣልያና ከጀርመን ጋር ባንድነት ተጠቃለው የሻርል ፭ኛ የንጉሠ ነገሥት ግዛት ናቸው ።

በመጨረሻ በደብዳቤያቸው መዝጊያ ላይ እኔ ገላውዴዎስ የላክሁትን ይኸን ጴጥሮስን ስለኔ ሆኖ የሚነግርህን ስማው ያሉት ሰውዬ ኢትዮጵያዊ ይሁን ፖርቱጋላዊ አለዚያም ሌላ የውጭ አገር መላክተኛ መሆኑን አናውቅም ። ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ነው የሚሉ አሉ ። አይመስልም ይኸን የመሰለውን ደብዳቤ ይዞ ለመሄድ የሚችልም የሚመረጥም ሁል ጊዜ የውጭ አገር ሰው ነው ።

በዚህ መጽሐፍ በ፲፩ና - በ፳፩ ምዕራፎች ላይ ስሙን የጠቀስነው ፖርቱጋሎቹ ፒድሮ ደ ኮቪልሀአ የሚሉት በእኛ ጽሑፍ ጴጥሮስ ተብሎ የሚጠራው ከዓፄ እስክንድር ዘመነ መንግሥት ዠምሮ (፲፱፻፸ ፲፱፻፹፯ ዓ. ም.) በኢትዮጵያ ብዙ

(1) ማቴ. ምዕራፍ 16 ቍጥር 19

ዘመን ከመቀመጡ የተነሣ እነ አልቫሬጽ የመጡ ጊዜ (፲፭፻፲፱ - ፲፭፻፳ ዓ. ም.) አስተርጓሚያቸው እንደነበረ ክርስቲያኖችም እስላሞችም አሕዛቦችም የሚናገሩ ባቸውን ቋንቋዎች አጣርቶ እንደሚያውቅ አልቫሬጽ የጻፈውን እናስታውሳ ለን (1) ።

ስለዚህ በወጣትነቱ ጊዜ የመዠመሪያውን የኢትዮጵያንና የፖርቱጋልን ግን ኙነት የከፈተው ይህ ጴጥሮስ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ አሁንም በሕይወት እስከዚህ ጊዜ ደርሶ በሽምግልናው ዘመን የዓፄ ገላውዴዎስን ደብዳቤ ለጳውሎስ ፫ኛ ይዞ ሄዶ ይሆናል ። ይሁን እንጂ ግምት ነው እንጂ ለዚህም የማረጋገጫ ሰነድ የለንም ።

## ምዕራፍ ፻፴፯

በቀሌምንጦስ ፯ኛ ምትክ የጳውሎስ ፫ኛ መሾም — የአውሮፓ ነገሥታት የርስ በርስ ጠብና በሉተር ቀስቃሽነት የተወጠነው የቤተ ክርስቲያን መሻሻል — ቤር ሙዴዝ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንዲለወጥ ስለመጠየቁ ።

በምዕራፍ ፹፯ ላይ ያዔ ልብነ ድንግልን መላክተኛ ፍራንቼስኮ አልቫሬጽን ተቀብ ለው ያነጋገሩ ቀሌምንጦስ ፯ኛ ይባሉ እንደነበረ አንብበናል ። እርሳቸው ከኢትዮ ጵያ ጉዳይ የባሰ ታላላቅ የአውሮፓ ጉዳይ ይኸውም ማለት በፈረንሳዊ ንጉሥ በፍራ ንሷ ፩ኛና በጀርመኑና በኤስፓኙ ንጉሠ ነገሥት በሻርል ፭ኛ መካከል የነበረው ጠብ ትልቁ የቱርክ ሱልጣን ሶሌይማን የአፍሪካን ሰሜን የአውሮፓን ምሥራቅ ወሮ የአውሮፓን የክርስቲያን ነገሥታት አስፈርቶ ስለነበረ ሁለቱን ጠበኞች አስ ማምቶ በእስላሙ በቱርኩ ፊት እንዲመክቱ በማድረግ ፈንታ ሶለይማንንና ፍራን ሷን ለማቀራረብ እንደሞከሩ ተገንዝበናል ። በዚህም ላይ ሉተርና ካልቪን የቀሰቀ ሱት የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት ጉድለትና የመሻሻል ጉዳይ ፤ የእንግሊዙ ንጉሥ ሐንሪ ፰ኛ የቀድሞ ሚስቱን ፈትቼ አዲስ ላግባ አታገባም የሚሉ ክርክር ተነሥቶ በሮማ በቫቲካኑና በእንግሊዝ ንጉሥ መካከል ጠቡ እየከረረ ሄዶ ምንም ውሳኔ ሳይገኝለት ቀሌምንጦስ እንደ አው. ቀ. መስከረም ፳፭ ቀን ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. ስለሞቱ አሁን እኚህ ዓፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤ የጻፉላቸው ሊቀ ጳጳስ የቀ ድሞ ስማቸው ካርዲናል አሌክሳንደር ፋርኔዝ ይባል የነበረው ጳውሎስ ሳልሣዊ ተብለው በመንበረ ጴጥሮስ በዚሁ ዓመት ጥቅምት ፲፫ ቀን ተቀመጡ (2) ።

እርሳቸውም ከክርስቲያኑ ከሻርል ፭ኛ አስፈሪነት ይልቅ የቱርኩ ሱልጣን የሶ ለይማን አያያዝ አስጊ መሆኑን ስለተረዱት የሹመት አባታቸው ለፍራንሷ እያደሉ ከሻርል ፭ኛ ጋር ይጣሉ የነበረውን የፈረንሳዊውን ንጉሥና የቱርኩንም ሱልጣን

(1) እነ አቶ ግርማ በሻህ ተርጉመው Centro de Estuides Historica Oltemari ያሳተመው የአልቫሬጽ መጽሐፍ ምዕራፍ 104 ፤ 112

(2) Histoire des papes- F. Hayward. ምዕ. 11 ገጽ 305

ለማቀራረብ የሞከሩትን መንገድ ትተው ሁለቱን የክርስቲያን ነገሥታት በ፲፭፻፴፰ ዓ. ም. አስታርቀው አብዛኛውም ጊዜ የሚጣሉባቸው የኢጣልያ አውራጃዎች ስለነበሩ በኢጣልያ ሰሜን የሚገኘው ሚላን (ሚላኖ) ለሻርል ፭ኛ ፤ ሳቡዋና ፒዬሞ (ሳቮያና ፒዬሞንቴ) ለፍራንሷ እንዲሆኑ ተወስኖ በዚሁ አስረቁዋቸው ።

በዚህ በኩል ሁለቱን ነገሥታት አስታርቀው ሁኔታው መሻሻል ሲጀምር ጳውሎስ ፫ኛ ከእንግሊዝ ንጉሥ ከሔንሪ ፰ኛ ጋር በጋብቻ ምክንያት የተቀሰቀሰው ጠብ እየባሰበት ሄደ ። የጠቡ ምክንያት ሔንሪ ፰ኛ የቀድሞ የሕግ ሚስቱን ካቴሪ ኒን ፈትቶ አን ቤሌይን የምትባለዋን ስላገባ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደንብ የሚ ስት ፍቺና ድጋሚ ጋብቻ ክልክል ስለሆነ ሔንሪ ፰ኛ ዝም ብሎ በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ስላገባና የእንግሊዝ ንግሥት ስላሰኛት በቀድሞውም በአሁኑም ሊቀ ጳጳስ ዘንድ የተወገዘ ሆኗል ። በዚሁ ንዴት የተነሣ ሔንሪ በግዛቱ ያሉትን ለጳጳሳቱና ለካቶ ሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚቀረቀሩትን እየያዘ በማሠርም በመግደልም ያጉላላ ዠመር ።

በዚህ መካከል ወደ ኢትዮጵያ ርዳታ የላከው የፖርቱጋል ንጉሥ ሚስቱ የሻርል ፭ኛ እኅት በመሆኗ በየጉዳዩ መግባቱ ባይቀርም በጠቅላላው ከሊቃነ ጳጳ ሳቱ ከፊተኛውም ከአሁኑም ተስማምቶ ከአባትና ከአያት የመጣለትን ሰፋፊ ግዛት ይገዛል ።

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ፖርቱጋል በአሁኑ ጊዜ በእስያ ሕንድን በደ ቡብ አሜሪካ ብራዚልን የሚያካክሉ ሰፋፊ ግዛቶች አሉት ። በአፍሪካም አሁን እለ ቅም ብሎ የሚዋጋባቸው የሞዛምቢክ የአንጎላ ግዛቶች በእጁ ናቸው ። ባለፈው እን ዳነበብነው ምንም የትእዛዙ ምንጭ ንጉሡ ዮሐንስ ካለበት ከዋናው ከተማ ከሊስ ቦን ቢወጣ ለኛ ጦር የመጣልን ከሕንድ ከጐአ ከተማ ነው ። ያመጣጣቸውንም ባለ ፈው በዝርዝር አንብበናል ።

ስለዚህ በዚህ በኢትዮጵያ ቤርሙዴዝ ጳጳስ ካልሆንሁ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን ተዋሀዶነቷን ትታ ካቶሊክ ትሁን ንጉሡ ለእስክንድርያ ፓትሪያርክ በመታ ዘዝ ፈንታ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ታዛዥ ይሁን እያለ በሚጣላበት ሰዓት በአውሮፓ የሊቀ ጳጳሱን አሳብ ይዞ ያወዛውዝ የነበረው ከዚህ በፊት የጠቀስነው እነ ሉተር የቀሰቀሱት የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓትና አስተዳደር የመሻሻል ጉዳይ ነው ። የሉተር አነሣሥ በጀርመኖችና በነምሳዎች ስለተደገፈ አሳቡም እያደር ስለተስፋ ፋና የፕሮቴስታንትን ጕራ ስለ አጸና ለዚሁ ጉዳይ ሊቀ ጳጳሱ ጳውሎስ ፫ኛ ከ፲፭፻ ፺፪ ዓ. ም. ዠምሮ በትራንት (ኢጣልያ) ስብሰባ እንዲደረግ አሳስበው ሳለ በየምክ ንያቱ ሳይቻል ቀርቶ ከ፲፭፻፺፯ - ፲፭፻፺፱ ዓ. ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ስብሰባው ስለ ቤተ ክርስቲያን መሻሻል ብዙ ውሳኔ ከወሰነ በኋላ በ፲፭፻፺፱ ዓ. ም. ኅዳር ፲ ቀን ሊቀ ጳጳሱ ጳውሎስ ሞተው ዩልዮስ ፫ኛ ተሾሙ ።

ስለዚህ ጴጥሮስ የተባለው ባለፈው ምዕራፍ ያነበብነውን ያቄ ገላውዴዎስን ደብዳቤ በምን አኳኋን አድርሶ ሊቀ ጳጳሱ በምን አኳኋን እንደተቀበሉት አናው ቅም ። የሆነ ሆኖ ወደፊት ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ጠቡን እያከ

ISIC

ረረው ሄዶ እስከ መዋጋት እስከ መጋዝ መድረሱን እርሱው ራሱ በመጽሐፉ የተ ወው ማስታወሻ ያመለክታል ።

በፊተኛው ከግራኝ አህመድ ሞት በፊት ከልብም ባይሆን ለሮማ ሊቀ ጳጳስ እታዘዛለሁ ብለው ስምምነት አድርገው የነበረውን ግራኝ ከሞተ በኋላ በሁለቱ መካከል ያለው ጠብ እየባሰበት ሄዷል ። ይልቁንም በበኩሉ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ እታ ዘዛለሁ ብሎ መጻፍና ማወጅ አይበቃም ፤ የማኅሌቱ ፤ የቅዳሴው ፤ የቁርባኑ ወግና ሥነ ሥርዓት ሁሉ እንደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሆን አለበት እያለ ክርክሩን በየቀኑ ባበዛው መጠን ጠቡ እየከረረ ሄዷል ።

ቀድሞ ለሮማ ሊቀ ጳጳስ እታዘዛለሁ ብለው ያወጁት ዮሐንስን ከመንበረ ጵጵ ስና ላይ አስቀመጥነው ያሉት ግራኝ ከመሞቱ በፊት የራሳቸው ግዛትም ቢሆን በስ ሜን በስደት ላይ በሥፈራቸው ሳሉ ነበር ። አሁን ግን ግራኝ በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. በየካ ቲት ፳፯ ቀን ከሞተ ወዲህ ከርሱ በኋላ በርሱ እግር ተተክቶ የደቡቡን ኢትዮጵያን ፈጠጋርን ፤ ደዋሮን ፤ ባሌን ሁሉ ይገዛ የነበረውን ወዚር አባስን በ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. አሸንፈው ከገደሉና በጠቅላላው ክርስቲያናዊው መንግሥታቸው ከተቋቋመ በኋላ እላይ እንዳልነው ብዙ ዘመናት የኖረው የኢትዮጵያ የቅዳሴው ፤ የቁርባኑ ፤ የክርስት ናው እንግሥ የጋብቻው ደንብና ሥርዓት ሁሉ እንደ ሮማ ቤተ ክርስቲያን ይሁን ብሎ ተነሣ ። እርሳቸውም በዚህ ጊዜ አንደኛ አስጊዎቹ ግራኝና ባለፈው ምዕራፍ እንዳነበብነው ወዚር አባስ ሞተው መንግሥታቸው ስለቆመ ፤ ሁለተኛ ራሳ ቸው ወድደው ቢቀበሉትም ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ካህናቱም በፍ ጹም ስለማይቀበሉት ፤ ሦስተኛ ፤ ያስፈራራባቸው የነበሩትን የፖርቱጋል ወታደ ሮች አጋማሾቹን ከነአለቃቸው በቀን ብዛት ወደርሳቸው ስበው ወገን ስለአደረጉዋ ቸው ጥያቄውን እምቢ ብለውታል ። የዚህን ጉዳይ እርስ ራሱ ራፖር ለራሱ ንጉሥ በሰጠበት ላይ መንግሥቱ ከተቋቋመ በኋላ በደንብ አዋጅ አድርጎ ለሮማ ቤተ ክርስ ቲያን ታዛዥነታቸውን አረጋግጠው የሥነ ሥርዓቱን መለወጥ ተስፋ አድርጌ ስጠ ባበቅ ባለፈው የሰጡት ተስፋ ያለልብ ስለነበረ እርሱን በፍጹም ረስተው የርሱን ተጻራሪ ያደርጉ ዠመር ሲል ገልጦታል (1) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማ ሊቀ ጳጳሳት የግራኝን ወረራ ለማስወገድ በተደረገው ትግል ወታደር ልከው የረዱዋቸው ርዳታ ነገሩ ገና ትኩስ ስለሆነ ሊዘነጋቸው አይችልም ። ራሱ ቤርሙዴዝም ከኢትዮጵያ ሕንድ ፤ ከሕንድ ሊስቦን ፤ ከሊስቦን ሕንድ ፤ ከሕንድ ወደ ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ የባሕርና የየብስ የጉዞ ችግር የቱርኮቹንና የዓረቦችን ቍጥጥር አልፎ በትጋት እነዚህን ወታ ደሮች ሲያመጣ ምንም እንኳን ጉዳዩን ለማከናወን የገፋው ኢትዮጵያን ካቶሊክ አደርጋለሁ እኔም በግብጻዊው ፈንታ ጳጳስ ሆኜ እከበራለሁ የሚለው ምኞት ቢሆ ንም ዞሮ ዞሮ በርሱ ድካም እነዚህ ወታደሮች መጥተው አብረዋቸው በመዋጋት ለግራኝ አወዳደቅ ዋና መሣሪያ ስለሆኗቸው ውለታው ለርሳቸውም ለእናታቸውም

(1) Hist. du christ. ገጽ 182

ለንግሥት ሰብለ ወንጌል ሊረሳቸው አይችልም ።

ነገር ግን የርሳቸው ምኞት እስላም እስላምን ሲረዳ በክርስቶስ ባሕርይ ተለያ ይተን በሁለት አብያተ ክርስቲያን ስም ቢጠራም ካቶሊክና ተዋሕዶ ያው ክርስቲ ያን ስለሆነ በተወጠነው ዝምድና መሠረት ክርስቲያኑ የፖርቱጋል መንግሥት የክ ርስቲያኒቱ ኢትዮጵያ መጠቃት ቆጭቶት ለርዳታ እንደደረሰላቸው ስለቆጠሩት እርሳቸውም ለዚህ ውለታ በካስታንሆ፡ ስንብት ጊዜ እንደተመለከትነው ለንጉ ሡም ለዮሐንስ የጻፉትን ደብዳቤ እንዳነበብነው ሁለቱ አገሮች የየግል ሃይማኖታ ቸውን ይዘው በወዳጅነት እንዲተሳሰሩ ፡ ሊዋጉ ከመጡት ፈረንጆች መመለስ የሚ ፈልጉትን በወርቅ ስጦታና በሽልማት አስደስተው ለመሸኘት ከርሳቸው ጋር ለሚ ቀሩት እንደዚሁ በሹመት በሽልማት በስጦታ ከማስደሰት ጋር ግለፈያ ግለፈያ ርስተ ጉልት እየሰጡ አንከባክበው ለማኖር ፡ ዮሐንስ ቤርሙዴዝም ለወገኖቹ ለፖ ርቱጋሎቹ ብቻ ጳጳስ መሆኑን ተቀብለው ሰፊ ግዛት ሰጥተው በክብሬታ ለማኖር ነበር እንጂ የርዳታው ዋጋ በሃይማኖት ለውጥ እንደሚሆን ተገድደው የሚጠየቁ በት መሆኑ ከመዠመሪያው ላይ የገባቸው አይመስልም ።

ነገር ግን ቤርሙዴዝ ለሮማ ቤተ ክርስቲያን መታዘዝ እምቢ ካልሁ ለርዳታ ያመጣሁዋቸውን ወታደሮች ይገፍ እመለሳለሁ ሲላቸው ባንድ ጊዜ ከካቶሊክ አገ ሮችም ከእስላሞችም ጠበኛ መሆናቸው ስለ አሰጋቸው ከዚህ ከሁለት የችግር አዘ ቅት ለመውጣት በመዠመሪያው ላይ አውጀውም ደብዳቤ ጽፈውም ለሮማ ቤተ ክርስቲያን እታዘዛለሁ ማለታቸውን ተመልክተናል ።

ዳሩ ግን በዚህ ጊዜ በተለይ ግራኝና አባስ ሞተው ቤርሙዴዝ በበኩሉ በልስ ላሴ ሳይሆን በኩራትና በቁጣ ይኸው የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲመሠረት ሥነ ሥር ዓቱ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንዲተካ እያለ ማስቸገሩን የተመለከቱ ከየአለበት የተሰበሰቡ የቤተ ክህነት አባቶች ሳይቀበሉት መቅረታቸውን ወደፊት በሰፊው እናነባለን ።

## ምዕራፍ ፻፴፰

### ፪ኛው የቤርሙዴዝ ጠብና ግዞቱ — ስለ ማርቆስ — ስለቤርሙዴዝ ወደ አገሩ መመለስ (፲፭፻፵፯ ዓ. ም.)

ቤርሙዴዝ በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ከወጣቱ ንጉሥ ከዓፄ ገላውዴዎስ በስሜን እንደተገ ናኙ የዚህኑ የሃይማኖት ክርክር ባነሣ ጊዜ የፖርቱጋሎቹ ሹም አልፎንሶ ካልደ ይራ የሚባለው ነበር ። ይኸም የጦር አለቃ ቤርሙዴዝና ገላውዴዎስ በሚከራከሩ በት ጊዜ አሳቡን ወደ ቤርሙዴዝ አድርጎ ሌሎቹንም ፖርቱጊዞች በማዘዝም በማ ሳደምም ለቤርሙዴዝ ዋና መካሪያ ሆኖት ነበር ።

አሁን ግን ባለፈው እንዳመለከትነው ከግራኝ ሞት በፊት እርሱ ከፈረስ ወድቆ ሲሞት በርሱ እግር የተሾመው ከዚህ በፊት ስሙን ደጋግመን ያነሣነው እር

ያስ ዲያዝ በኋላ ማርቆስ ተብሎ የተሠየመው ነው ። ከግራኝ ጋር በተደረገው ጦር ነት ላይ የፖርቱጋሎቹ አዝማች እርሱ እንደመሆኑ መጠን እውነተኛውንም ጉዳይ ጴጥሮስ የልዮኑን ለንጉሡ አቅርቦ ያሸለመ እርሱ ነው ። ይኸም የጦር መኰንን ከመዠመሪያ ጊዜ ዠምሮ ከንጉሡ ጋር በደንብ ስለተዋወቀ አሁን ከግራኝ ሞት ወዲህ ዓፄ ገላውዴዎስ ይኸን ሰውዬ በሹመትም በሽልማትም በክብርም አስደስ ተው የራሳቸው ባለሟል አድርገውታል ። ባለሟልነቱና ወዳጅነቱም ሲጸና ቤርሙ ዴዝ የንጉሡንና የጠቅላላ ያገሪቱን ካቶሊክ መሆን በሚጠይቅበት ጊዜ አርያስ ዲያዝ እንደገና ከካቶሊክነት በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖት ገብቶ በኢትዮጵያ ስነ ሥርዓት ክርስትና ተነሥቶ ስሙ ማርቆስ ተብሎ ሕዝቡም ንጉሡም የሚጠሩት ማርቆስ እያሉ ነው ።

ማርቆስ ስለ ክርስቶስ በግብፅ የተገደለው ወንጌላዊ የእስክንድርያ መንበር ጌታ ስለሆነ አርያስ ዲያዝ በርሱ ይሠየም ተብሎ መሠየሙ በተለይ በዚህ ሰዓት ልዩ ትርጓሜና ስሜት አለው ። በደቡቡ ክፍል በግራኝ ምትክ ሆኖ የተዋጋው አባስ በውጊያ ሞቶ ሚስቱ የተማረከች ጊዜ ክርስትና ተነሥታ በንጉሡ ፈቃድ ለርሱ መዳሯን ማርቆስም ከአባስ ሞት ወዲህ ትልቁን የደዋሮን አገር መሾሙን እንብበ ናል ።

ስለዚህ ንጉሡ ከሃይማኖት ጉዳይ አልፈው ደግሞ በኢትዮጵያ የፖርቱጋል ንጉሥ ባንዲራ መያዝ አለ[SIC]እያሉ ቤርሙዴዝና አንዳንድ ፖርቱጋሎች ሲያስቸ ግሩ ማርቆስ የሚከተሉትን ፖርቱጋሎች እንደያዘ ከንጉሡ ወገን ነበር ። በዚህ ምክንያት ዓፄ ገላውዴዎስ በዘዴ ቤርሙዴዝ የሚመካባቸውን ፖርቱጋሎች ወደ ርሳቸው በማድረግ የርሱን ጕራ ሲያዳክሙ እርሱ ደግሞ ወደ ንጉሡ የዞሩትን ፖር ቱጋሎች ከዳተኞች ከርሱ ጋር ያሉትን ታማኞች እያለ በሁለቱ መካከል ያለው ጠብ አላቋረጠም ።

ካስታንሆዞ ሲመለስ አብረውት ሃምሳ ፖርቱጊዞች መመለሳቸውንና ካፄ ገላ ውዴዎስ ጋር የቀሩትን ቍጥር 120 አድርጎት እንደነበር እናስታውሳለን ። አሁን ቤርሙዴዝ በኢትዮጵያ ያሉትን የፖርቱጋሎች ቍጥር 150 አድርጎታል (1) ። በዚህ በሃይማኖትና በሰንደቅ ዓላማ ጠብ ሰዓት ምን ያህሉ ከቤርሙዴዝ ጋር እንደሆኑ ምን ያህሉ ከአለቃቸው ከማርቆስ ጋር ሆነው በንጉሡ ዙሪያ እንደተሰለፉ አናው ቅም ።

የሆነ ሆኖ ቤርሙዴዝ በመጽሐፉ እንደሚለው ንጉሡ ገላውዴዎስ በማዘቱ የኔን ሰንደቅ ዓላማ እንጂ የፖርቱጋልን ንጉሥ ሰንደቅ ዓላማ አትያዝ ብለው ማር ቆስን ማዘዛቸውንና ሰንደቅ ዓላማውን ከፖርቱጊዞች ለማስጣል አንድ የኢትዮጵያ መኰንን ሲይዘው ዢክ ደብሬቶ የሚባለው የፖርቱጋል ተወላጅ በሰይፉ ተማትቶ ማስጣሉን እንደዚሁም ቤርሙዴዝ በሌላውም በዚህም ነገር በኃይል እየተናገረ መቆጣቱን ሲያይ ማርቆስ ሄዶ «ካገራችን ርቀን በዚህ አገር ባለንበት ጊዜ ንጉሡን

(1) Hist. du Christ. ገጽ 182

ገላውዴዎስን በኃይለ ቃል ንግግርና በቁጣ ማናደድ ጥቅሙ ምን እንደሆነ አይገባኝም» ብሎ ቤርሙዴዝን እያዘነ ሲወቅስ አንዳንድ ፖርቱጋሎች ከመቀመጫቸው እየተነሡ «አንተ የፖርቱጋልን ንጉሥና ዘውድ ከድተሃልና እንግዲህ የፖርቱጋል ሹም አይደለህም» ቢሉት እሱም መልሶ «የአገሩ ንጉሠ ነገሥት ሹም ነኝ እንጂ የፖርቱጋል ንጉሥ ሹም አይደለሁም ይኸም ከዳተኛ አያሰኘኝም» ብሎ መልስ መስጠቱን ይገልጻል (1) ።

ከዚህ በኋላ በዚህ ዓይነት ግማሾቹ ከማርቆስ ጋር ሆነው ለንጉሡ ታማኝ አገልጋይ ሲሆኑ የቀሩት ምናልባት ጥቂቶቹ ከቤርሙዴዝ ጋር ሆነው በየጊዜው ጠብና ጭቅጭቁ አልበርድ ስላለ ቤርሙዴዝ የሚለው የታመነ እንደሆን ፖርቱጋሎቹና ኢትዮጵያውያኑ ጦርነት እስከማድረግ ስለደረሱ ዓፄ ገላውዴዎስ ቤርሙዴዝንና ከርሱ ጋር ያሉትን ፖርቱጊዞች በሹመት መልክ ከፋፍለው በመደልደል በያለበት እንዲበተኑ አደረጓቸው ። እርሱንም ራሱን የጋፋትን ግዛት ሰጥተው በግዞት መልክ ወደዚያ ልከውት ከዚያ ያለፈቃዳቸው እንዳይወጣ አደረጉ ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ከጋሎች ጋር ሲዋጉ ዘምተው ከተመለሱ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ማርቆስ መሞቱን በማርቆስ ሞት ንጉሡ ከአባታቸውና ከወንድማቸው ሞት አብልጠው እንዳዘኑና በታላቅ ሥነ ሥርዓትና በዓል ነገሥታቱ በሚቀበሩበት ቤተ ክርስቲያን ስለ አስቀበሩት ቤርሙዴዝ ስለሰማ በጋፋት ፪ ወር ከተቀመጠ በኋላ ጠባቂዎቹን አታሎና አስፈራርቶ ወደ ንጉሡ ሲጓዝ ፍራንሲ ማጀላን የሚባለውን የፖርቱጋልን ተወላጅ ንጉሡ የሰጡትን ጉልት ለመጐብኘት ISIC ጨጣ ከመንገድ ተገናኝተው በማርቆስ እግር ኀርከ ዶ ፊጊርዶ መሾሙን እርሱም ታሞ ወዲያው ስለሞተ ካስፖር ዶ ስፉንና ሎፒ ዳልማንሳ የሚባሉትን የቀኝና የግራ ሹማምንት አድርገው ንጉሡ መሾማቸውን ከርሱ እንደሰማ ጉዞውን ቀጥሎ ንጉሡ ካሉበት ሠፈር ሲደርስ ዓፄ ገላውዴዎስ ለምን ያለ ፈቃዴ መጣህ ብለው በመቆጣት ፊንታ ደህና አቀባበል እንዳደረጉለት ያመለክታል ።

በዚህ መካከል ዓፄ ገላውዴዎስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቤርሙዴዝን የካቶሊኩን ጳጳስነት እንደማትቀበል በማወቅ ቀጥሎ ባፄ ልብነ ድንግል ዘመን የነበሩት አባ ማርቆስ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ላይ ሞተው እስከዚህ ጊዜ ድረስ (፲፭፻፵ ዓ.ም.) ፲፰ ዓመት ሙሉ አገሪቱ ያለ ጳጳስ ስለኖረች ጳጳስም ከሌለ ክህነት ዲቁናና ቅስና የሚሰጥ ከጳጳስ በቀር ሌላ ስለሌለ በተለይ አሁን የእስላሞቹ ሥልጣን ወድቆ ክርስትና በሚቋቋምበት ሰዓት በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን ችግር በመመልከት ከማርቆስ ጋር በመስማማት ጭምር ከእስክንድርያ ፓትሪያርክ ተላልከው ያስመጡዋቸው ግብጻዊ ጳጳስ ምጥዋ ገቡ ። ከዚያ አልፈው ደባርዋ መግባታቸውን ንጉሡ ስለሰሙ የርሳቸው አመጣጥ ለጊዜው ጠብ እንዳያበቅል ቤርሙዴዝ እንዳይሰማ በምሥጢር ይያዝ ተብሎ ኖሯል ። ቤርሙዴዝ ግን የጳጳሱን መምጣት ንጉሡ

(1) Hist. du Christ. ገጽ 186

እርሳቸውን ለመቀበል መዘጋጀታቸውን አዝማች ሮቤል የሚባለው በድብቅ መጥቶ ነገረኝ ይላል ። ምናልባት ይህ ሰውዬ ለቤርሙዴዝ ይኸን ምሥጢር መና ገሩ በሹመት ወይም ባንድ ምክንያት በንጉሡ ላይ ቅሬታ አድሮበት ይሆናል ።

ንጉሡ ጳጳሱን ለብቻ ተዘጋጅተው በሚቀበሉበት ሥፍራ በሰላይ እንደሰማው እምባ ጓሮ ለማንሣት ያለፈቃዳቸው ወደርሳቸው መሄዱን ሰምተው አስያዙት ወዲያውም በዚህ ሰውዬ ላይ ትዕግሥታቸው አልቆ አሥረው ወደ አንድ ተራ ራማ አገር ሊሰዱት ሲሉ ገላጋይ ገብቶ ስለ አማለደ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የመጡት ግብጻዊ ጳጳስ የኛ አባት ናቸው ። አንተ ግን የፈረንጆቹ (የካቶሊኮቹ) ጳጳስ ነህ ብለው አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ወስነው እሥራቱ ቀረለት ።

ከዚህ በኋላ በቤተ አምሐራ አዲስ የመጡት ጳጳስ አባ ዮሳብ (1) ክብረ በዓል ተደርጎ የጵጵስናቸውን ሥፍራ እንዲወርሱ ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ ምክር ተደ ርጎ ቤርሙዴዝና ወገኖቹ ፖርቱጋሎች ወደ ደዋሮ አሁንም በሹመት መልክ ተሳ ኩና የጳጳሱ በዓለ ጵጵስና በሰላምና በጸጥታ ተከበረ ።

ይህ ጊዜ የጋላ ወረራ ከታች ከሱማሌና ከቦረና ወደላይ እየገፋ ያስቸገረበት ጊዜ ነበር ። በዚህ ጊዜ ዋናው የፖርቱጋሎቹ አዝማች ማርቆስና ንጉሡም ጭምር ከጋላ እየተዋጉ ብዙ ሰው አልቆ ማርቆስም የሞተው በዚህ ጦርነት በቆሰለው ቁስል ነው ።

ይሁን እንጂ ቤርሞ[illegible] በጠቅላላው በኢትዮጵያ ፴ ዓመት ያህል ስለተቀ መጠ ያገሩን የባላገሩን ስሜት በማወቅ ንጉሡ ቃላቸውን አፍርሰው ግብፃዊ ጳጳስ ስለአስመጡ እግዚአብሔር ተቆጥቶ የጋላን ወረራ አስነሣባቸው የሚል ስብከት ከወገኖቹ ጋር ለመንዛት ሞክሯል ። ከርሱ ጋር ያሉት ወገኖቹ ፖርቱጋሎቹም እርሱ በጵጵስናው ሥፍራ ቢመለስና ከጋሎቹ ጋር ብንዋጋ ይቀናናል እስከማለት ደርሰዋል ።

ንጉሡ ግን የጋላ ወረራ አደገኝነት ምንም እንኳን ባይሳታቸው የነቤርሙ ዴዝ ስብከት ከንቱ መሆኑን በመረዳት አሳባቸውን ለውጠው ቤርሙዴዝን ጳጳስ ለማድረግ ይልቁንም ጳጳስ ከግብፅ መጥቶ ሹመቱን በያዘበት ጊዜ በፍጹም አልከጀሉም ። ቤርሙዴዝም በዚህ በጠቡና በኩርፊያው እንዳለ ወዳገሩ ተመልሶ ከሮማ ጳጳስና ከፖርቱጋል ንጉሥ ያጣላኛል ብለው በመስጋት ሳይሆን አይቀርም በደቡብ በነበሩበት ሰዓት ከርሳቸው ሳይለዩ በጉራጌ በእናሪያ በወሊጋ በቤኒ ሻን ጉል በዳሞት በጋፋት ዞረው በመጨረሻ ወደቤተ ማርያም ተመለሱ ።

በዚህ ጊዜ በደዋሮ በየአውራጃው ሥሪት የተመሩት ፖርቱጋሎች አሁን ግን ጋላ ደዋሮን ስለወረረው ከደቡቡ ክፍል ከንጉሡ ጋር ተመልሰው በዚሁ በቤተ ማር ያም (የአማራ አገር) ርስት እየተመሩ ተቀመጡ ።

ቤርሙዴዝም በቤተ አምሐራ ትንሽ ጊዜ እንደተቀመጠ በዚህ ጊዜ በንጉሡ ትእዛዝ የፖርቱጋሎቹ አለቃ ካስፖር ደ ሶፋ ሲያስጠብቀው ለማታለል ሳይታመም

(1) ቤርሙዴዝ በስሕተት አባ ዮሴፍ ብሏቸዋል ገጽ 211

ታምሚያለሁ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄጄ ስለነፍሴ እጸልያለሁ (1) ብሎ ከጠባቂዎች አታሎ ወደ ደባርዋ ሄደ ። በዚያም የርሱንና የፖርቱጋሎችን ሁኔታ ለመመርመር ከሕንድ አገር ተልኮ ከመጣው ከጎንዛሌስ (ጎንሳልቭ) ጋር ተገናኝቶ በደባርዋ ሁለት ዓመት ያህል ተቀምጦ ከደባርዋ ወደ ሕንድ መሄዱን ከሕንድ ወደ ፖርቱጋል ተመልሶ እንደ አው. ቍጥር በነሐሴ ወር ፲፭፻፶፱ ዓ. ም. ሊስቦን ማግባቱን በጽሑፉ ያረጋግጣል (2) ።

መቼም ቤርሙዴዝ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር በዚህ ዓይነት ያነሣውን ጠብና ክርክር ብዙ የአውሮፓ ጸሐፊዎች ነቅፈውታል ። ከሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በትክክል የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ለመሾሙ በፍጹም ሰነድ ስለሌለ ከሊቀ ጳጳሱም አመጣሁ ያለው ሙሉ ሰነድ ከግራኝ ጋር በተደረገው ጦርነት ክርስቶፎሮስ የተማረከ ዕለት ጠፋ ያለውንም እንደ የሐሰት ወሬ በመቁጠር የነቀፈው ሞልቷል ።

በተለይ ደግሞ ባገሩ ንጉሡ ንጉሥ ላይ ያላገባብ በኃይል ስድብም እየጨመረ መቆጣቱ ፤ ደግ ነው ጳጳስ ነህ ከተባለ በኋላ በፊት የደቆነው ዲያቆን የቀሰሰው ቄስ ሁሉ በኔ ቅስናውንና ዲቍናውን ያሳድስ ሥርዓቱ ሁሉ እንደ ሮማ ቤተ ክርስቲያን ይሁን ብሎ ያበቀለው ጠብ ሁሉ አስወቅሶታል ።

ከኢትዮጵያ በደባርዋ በኩል ተደብቆ ወደ ሕንድ ከዚያም ወደ ሊስቦን የገባበትን እርሱ ከላይ ባመለከትነው ዓይነት ሲተርከው አንዳንድ ጸሐፊዎች ከሮማ ደንበኞቹ መልክተኞች እነ አንድሬያ አቪዬዶ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት መነሣታቸውን ስለሰማ እነርሱ ደርሰው አታላይነቱንና ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ዘንድ በደንብ ያልተሾመ መሆኑን እንዳይገልጡበት እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት ጠፍቶ ተመለሰ ። አገሩም ከገባ ወዲህ በተራና በመጠነኛ ኑሮ ነው የኖረው እያሉ ጽፈዋል (3) ። ሊስቦን በ፲፭፻፶፱ ዓ. ም. ከገባ በኋላ ፲፮ ዓመት ያህል ኖሮ በተወለደ በ፸፫ ዓመቱ እንደ አው. ቍጥር በ፲፭፻፸፭ ዓ. ም. ሞተ (4) ።

(1) የሺምዛናው ደብረ ሊባኖስ (አባ መጣዕ) ሳይሆን አይቀርም

(2) Histoire du Christ. ገጽ 186 - 260

(3) Histoire de l'Abissinie-Jones-Monroe. ገጽ 119 - 120

(4) Biblioteca-Bio-Bibliografica-tom 1 partie 1 Etiopica francescana cafra-Teodosio... ገጽ 159 ። Morie Hist. d'Ethiopie Tome 2 ገጽ 257 - 259 ።

## ምዕራፍ ፻፴፱

## የዓጼ ገላውዴዎስ ኢትዮጵያ ከፖርቱጋልና ከቱርክ በቀል የዳነችባቸው ሰበቦች

ኢትዮጵያ ወደ አንድ መከራ የምትገባበት ምክንያት ሲታይ ከገባች በኋላ ደግሞ የመውጫ መንገድና ምክንያት እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይፈጥርላታል ። ኢጣልያ በ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ሰሜኑን ክፍል ከአውስትሪያ ተዋግታ የተከፋፈለውን የደ ቡቡን ባንድነት በመጠቅለል ነፃነቷን ካቋቋመች በኋላ ራሷ ደግሞ ሌላውን የመግ ዛት ምኞት እንደ እንግሊዝና እንደ ፈረንሳዊ እንደ ጀርመንና እንደ ቤልዥክ ቅኝ አገር ማግኘት አማራት ።

ስለዚህ የቅኝ ገዥዎች መሰማሪያ ወደሆነው ወደ አፍሪካ ፊቷን ብትመልስ ብዙውን ክፍል ሌሎቹ ተቀራምተውት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ በነፃነት መቀ መጣቸውን ተገነዘበች ። ባንድ ወገን ላይቤሪያ ሩቅ ከመሆኑ በላይ በአሜሪካ የተጠ በቀ ስለሆነ ለሜዲቴራኔያ የምትቀርብ ሀብት ያለባት አገር ኢትዮጵያ ስለሆነች ወደ ቦቿንም ቱርኮች ሲለቁ በነርሱ እግር ለመግባት የእንግሊዝ ድጋፍ ስለተገኘ በማና ቸውም ረገድ ኢትዮጵያን ለመያዝ ወሰነችና ካዜ ዮሐንስ ጋር ውጊያ ዠመረች ። በመካከሉ ዓፄ ዮሐንስ ሲሞቱ ጠቡ ካዜ ምኒልክ ጋር ሆነና የዓድዋን ጦርነ ትና ድል ወለደ ። በዚህ መካከል ለኢትዮጵያ መውጫ የፈረንሳዊን መንግሥት ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ቷሯፎቶ ኢትዮጵያን በአሳብም በመሣሪያም እንዲረዳ የፖ ለቲካው አዝማሚያ አስገደደው ።

የዓድዋን ብድር ለመመለስ ወዲያውም ለነክሪስፒ ያልተሳካውን የቅኝ አገር አመሠራረት ለመፈጸም ቤኒቶ ሙሶሊኒ በተነሣ ጊዜ አገሪቱንም ለመውረር በቻለ በትና ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ በመሰለበት ወቅት ሂትለር በአውሮፓ ጦርነት አነሣ ከርሱም ጋር የኛ ጠላት ኢጣልያ ከጀርመን ጋር ተደረበ ። እርሱ ከጀርመን ሲደረብና ጠላታችን ጠላታቸው ሲሆን ቀድሞ የነፈጉንን ርዳታ የባለ ቃል ኪዳን ጓደኞቹ እነ እንግሊዝ ሊሰጡን ውዴታም ግዴታም ሆነና በዚሁ ሰበብ ንጉሠ ነገሥ ታችን በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ገብተው ነፃነታችንን ለማግኘት ቻልን ።

አሁንም እነሆ በዚህ በአለፉት ምዕራፎች ዓፄ ገላውዴዎስ ኃይልም ዘዴም እያፈራረቁ ከዘመድ ጠላታቸው ከቤርሙዴዝ ተገላግለው የወረሱትን የስደት መን ግሥት በደንብ ማቋቋም ብቻ ሳይሆን ባለፈው እንዳነበብነው በእስላምና በካቶሊክ መካከል ተጨፍልቆ ሊሞት የነበረውን የተዋሕዶ ሃይማኖት በጠቡ መካከል ተላ ልከው ከእስክንድርያ ጳጳስ በማስመጣት ነፍስ ዘርተው በአዲስ ሕይወት እንዲነሣ አድርገው ወድቃ የነበረችውን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን መልሰው አቋቋሙ።

ንግሥት ሰብለ ወንጌልና ዓፄ ገላውዴዎስ እንደዚሁም ስማቸውንና ድካማቸ ውን የማናውቀው አማካሪዎቻቸው በዚህ ከቤርሙዴዝ ጋር በተደረገው ጠብ የሠ ሩት ዘዴ ከፍ ያለ ነው ። ግራኝ አህመድ ከመሞቱ በፊት ቤርሙዴዝ ለሮማ ጳጳስ ታዘዙ ያለዘያ ያመጣኋቸውን ፖርቱጊዞች ይገፔ እመለሳለሁ ባለ ጊዜ ነገሩን በቀዘ ዘቀ መንፈስ እመዛዝነው በልስላሴ ፈቃዱን ለጊዜው እሺ ብለው ፖርቱጊዞቹ ከግ

ISTC

ራኝ አህመድ ጋር በተደረገው ጦርነት እንዲካፈሉ ማድረጋቸው ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ዋና አብነት መሆኑን ያለነርሱም ጥይት ግራኝ የማይበገር መሆኑን ለማመዛዘን አያዳግትም ። ሁኔታው ብልጠትና ክዳት አለበት ቢባልም ይኸን የመሰለው ዘዴ በመንግሥታዊ እርምጃ በሌሎችም ዘንድ ሲፈጸም የኖረ ነው ።

እሺ በማለት ፈንታ እምቢ ብለው የጠበንጃ መሣሪያ የያዙት ፖርቱጊዞች ወደ ምጥዋ ቢመለሱ ኖሮ የግራኝ አህመድ ወረራ ዕድሜውን ለመቀጠል ዕድል ያገኝ ነበር ። በአጠገቡ ያሉት ፱፻ የቱርክ ባለ ጠበንጃና ባለመድፍ ወታደሮች ባዔ ገላውዴዎስ የሰይፈኛና የጦረኛ ወታደሮች ሊበገሩ ባልቻሉ ። ይህ ቢሆን ኖሮ ግራኝ ብዙ ጦር በነበራቸው ባዔ ልብነ ድንግል ጊዜ ሊሸነፍ በቻለ ነበር ። የመጀመሪያዎቹን ድሎች እንደ ተአምራት ካገኘ በኋላ የመጨረሻዎቹን ድሎች ደምድሞ ሊያገናኛቸው የቻለው ከውጭ ባገኘው ርዳታ ነው ።

እዚህ ላይ ደግሞ የእግዚአብሔርን ምሥጢራዊ መንገድ የምንመለከተው በወፍላ ጦርነት የግራኝን አሸናፊነት የክርስቶፎሮስን ተሸናፊነት ነው ። በወፍላ ጦርነት ክርስቶፎሮስ ደጋግሞ ጦርነቱን አሸንፎ በርሱ መሪነት ግራኝ ሞቶ ቢሆን ኖሮ በአሸናፊው በደጋግማና ገና ባልተደላደሉት ወጣት ንጉሥ በገላውዴዎስ መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት ምን ዓይነት መሆኑን በትክክል አናውቅም ። አሸናፊው ክርስቶፎሮስ ለዓጼ ገላውዴዎስ በሰላምና በጸጥታ ይታዘዝ ነበርን ወይስ ግራኝን በመግደሉ የበለጠ ኩራትና ትምክህት አድሮበት ከቤርሙዴዝ ጋር በመተባበር ከፍ ያለ የፖለቲካና ያገር ክፍያ ጠብ በበኩሉ ያበቅል ነበርን በቤርሙዴዝና በንጉሡ መካከል በተነሣው ጠብ ከማናቸው ወገን ይሆን ነበር ብለን እንዳንጠራጠር ቤተ ሰቡ የካቶሊክ ቤተ ሰብ ፤ አባቱ ቫስኮ ደጋማ የፖርቱጋል ከፍ ያለ የመርከበኛ መኰንን ፤ የመጀመሪያው የሕንድ እንደራሴ ፤ ወንድሙ በአሁኑ ሰዓት የሕንድ ጠቅላይ ገዥ ሲሆን በማናቸውም በአካሉም በመንፈሱም ከፖርቱጋል ንጉሣዊ ቤተ ሰብና መንግሥት እንደዚሁም ከካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር በጥብቅ የተሣሠረ ሰው በመሆኑ ጕራውን ከቤርሙዴዝ ጋር አድርጎ ስለ ካቶሊክ ሃይማኖት ጠብ ማንሣቱን እንኳን ብንጠራጠር ስለ ባንዲራው ስለአገሪቱ ሥልጣን ከንጉሡ ጋር መጣላቱ አይቀርም ነበር ። እርሱ በሕይወት እያለም ማርቆስ የተባለው አሪያስ ዲያዝና ሌሎቹም ከርሱ ተለይተው ወደ ንጉሡ ለመደረብ የሚደፍሩ አይመስልም። ወደ ንጉሡ እነርሱን ለመደረብ ያስገደደው ምክንያት የርሱ ሞትና የሁኔታው ተስፋ አስቆራጭነት የንጉሡ ነገሥቱም ባለሥልጣንነት ተደራርቦ ነው ።

ስለዚህ ከዚህ በፊት እንዳልነው እግዚአብሔር አውቆ የፖርቱጋሎች ኩራትና ትምክህት እንዳይበዛ በወፍላ እንዲሸነፉ አደረጋቸው ። ዓጼ ገላውዴዎስም በበኩላቸው ግራኝን እኔ ወይም የእኔ ሰው አጠፋው ብለው ለርዳታ በመጣት ፖርቱጋሎች ላይ ፈጽመው እንዳይታበዩ በርሳቸው የበላይ መሪነት ቢሆንም የግራኝን የገዳይነት ዕድል ባንድ ተራ የፖርቱጋል ተወላጅ እጅ አደረገው ። ነገሩን ሲመለከቱት ከላይ በትክክል ተመዛዝኖ የተሰጠ ትክክለኛና አምላካዊ ሒሣብ ይመስላል ።

ከዚህም ጋር የኢትዮጵያ ንጉሥ ቃሉን ለወጠ ብሎ የፖርቱጋል ንጉሥ በኢት

ISIC

ዮጵያ ላይ የመበቀል ጊዜ እንዳይኖረው ይህ መንግሥት ዮሐንስ ፫ኛ እንደ አው. ቍጥር በ፲፭፻፶፯ ዓ. ም. ሲሞት መንግሥቱ እየተዳከመ ሄደ ። ከርሱ ቀጥሎ ቤርሙዴዝ ባለፈው በየጽሑፉ የጠቀስነውንና ላክሮዝ ያሳተመውን ጽሑፍ በራፖር መልክ ያቀረበለት ሰብስትያኖስ ወዲያው እንደነገሠ በማሮክ ሲዋጋ በ፲፭፻፸፰ ዓ.ም. ሞተ ። እርሱ በሞተበት ዓመት ካርዲናል ሔንሪ የሚባለው ካህን የዮሐንስ ፫ኛ ወንድም መንግሥቱን እንደያዘ ከዚያም ከጐናቸው ፊልጶስ ዳግማዊ የሚባለው የኤስፓኝ ንጉሥ በታላቅ የግዛት ምኞት ተነሥቶ ፖርቱጋልን በመጠቅለል ጭምር እየቀናው ስለሄደ በዚህ በኢትዮጵያ በኩል ያለውን ጉዳይ የፖርቱጋል መንግሥት እንኳን ለመመልከትና ለመቆጣጠር የራሱንም መንግሥት በቀድሞው አቅዋም እንደጨበጠ ለመቆየት ሳይችል ቀረ ።

ባንድ ወገን ደግሞ ግራኝ አህመድ በፖርቱጋል ርዳታ ጭምር ሞቶ ፲፭ ዓመታት ያህል ዕድሜ በማግኘት በኢትዮጵያ የተወጠነው የእስላም መንግሥት ተነቅሎ ነዋሪው የክርስቲያን መንግሥት ሲደላደል በሩቅ ያለው የቱርክ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ አዲስ ጦር ልኮ የግራኝንና ከርሱ ጋር የሞቱትን የቱርኮች ደም እንዳይበቀል ወይም የእስላም መንግሥት ለማቋቋም እንዳይሞክር በፊቱ ያለው የሰፊው ግዛትና ያስተዳደሩ ጣጣ ይዞታል ። በአውሮፓ በባልካን ሰፊ ግዛቱ በግሪክ ፤ በሰርቢያ ፤ በሆንግሪ የተገዙት መልሰው እየሸፈቱ ያስቸግሩታል ። በምሥራቅ የፋርስ መንግሥ[illegible]ንደቀሩት ለመግዛት እልምበረከክም ብሎ ከርሱ ጋር በየጊዜው በመዋጋት ኃይሉን ስለቀነሰበት በወዲህ የኢትዮጵያን ጉዳይ ለመመልከት ጊዜ አላገኘም ።

በአውሮፓም የፖርቱጋል መንግሥት ደክሞ በሜዲቴራኒ በመካከለኛው ምሥራቅ ወደቦች እንደ ልቡ እንዳይሆን በነምሳና በሐንጋሪ ግንባር በሻርል ፭ኛ ሞት ጉዳዩ እንዳይገራለት ለማናቸውም በዚህ ጊዜ የኤስፓኙ ንጉሥ ፊልጶስ ዳግማዊ ባዲስ ጉልበት ስለተነሣ ሶሌይማን የልቡን ሊሠራ አልቻለም ።

ከሁሉ የበለጠ ደግሞ ሱልጣን ሶሌይማን እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፳ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ ፲፭፻፷፮ ዓ. ም. ድረስ ፵፮ ዓመት ስለገዛ በዚህ በመጨረሻዎቹ የአሥር ዓመት ግዛቶቹ ላይ እርጅናው ድካሙ ስለታወቀ የጦር አለቆቹ ይህ አርጌ ንጉሥ ( PADISHAH ) ለምን ዙፋኑን ለልጁ ለሙስጠፋ አይለቅም እያሉ ይወቅሱታል ። በዚሁም በወለደው ለግዛት ደርሶ ጦር በሚመራውና ስመ ጥር በሆነው ልጁ ቅናት አድሮበት ሻንቅላ ዘበኞቹን አዞ አስገደለው ። በርሱ አሳዛኝ ሞት ወታደርና የጦር አለቆች በአርጌው ሶሊማን ላይ ጥላቻም ትዝብትም አድሮባቸው. ነበር ።

ነገር ግን ምንም ሳይሆን በሚቀጥለው ጊዜ ማልታን ለማስገበር የመርከብ ጦር ልኮ ሲያዋጋ ቆይቶ በሚጥል በሽታ ( APOPLEXIE ) ሞተ (1) ።

በቅርብ ያሉት የርሱ ተገዥዎች የግብፅና የዘቢድ ፓሻዎች ኑሮአቸው ከዋ

(1) Soliman le magnifique . . . . . . . . ገጽ 241 - 243 ።

ናው የሱልጣን ሕይወት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በውስጣቸውም በነርሱ ዘንድ ፍጹም ዕረፍትና ሰላም አልነበረም ። በዚህ ምክንያት በዘቢድ ፓሻ ዘንድ ነበሩ የሚባሉት ፫ሺ በደንብ የታጠቁት የቱርክ ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያም ወደ ሌላም ክፍል ለጦርነት ወይም ላገር ጥበቃ እየተላኩ ቁጥራቸው ስለመነመነ የዘቢድ ፓሻ የግራኝ አህመድን ሞት ከሰማ በኋላ ከእነዚህ ወታደሮች በብዛት በወጅ ተዋግቶ ለሞተው ለወዚር አባስ ልኮ የግራኝን ሞት ለመበቀል ኢትዮጵያንም ሊገዛ ወይም ሊያስገዛ አልቻለም ። የዚህ ሁሉ ሁኔታ ኢትዮጵያን ረድቷል ፤ ወደፊትም ይኸን የመሳሰለ ዕድል ከኢትዮጵያ እንዳይለይ የአምላክ ፈቃድ ይሁን ።

ዳሩ ግን እነጎንዛሎ በመጡበት ዓመት ፲፭፻፶፭ ዓ.ም. የቱርክ መንግሥት ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ምጥዋንና አካባቢውን ይዞ ክርስቶፎሮስ ይዟቸው እንደ መጡ ያሉ ወታደሮች ሁለተኛ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ዘግቷል ። እነዚህም የቱርክ ወታደሮች ምንም እንኳን አገሪቱን በሙላ ለመውረር ባይችሉ ከምጥዋ እየ ተነሡ ወደ ደባርዋ ወደ ሠራዬ እየገቡ ማስቸገራቸው አልቀረም ። ይኸም ሁኔታ እስከ ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ድረስ ቀጥሎ መቆየቱን እናስታውሳለን ።

## ምዕራፍ ፻፵

በሮማ ጳውሎስ ፫ኛ ሞተው ዩልዮስ ፫ኛ ስ፲፻፭፻፶ሾማቸው — የኢየሱሳውያን ማኅበር መቋቋምና የሮድሪግ ጎንዛሎ በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (1) ።

(፲፭፻፵፫ ዓመተ ምሕረት)

የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፫ኛ ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው የጀርመኑ ተወላጅና ቄስ ማርቲን ሉተር በሮማ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በሥነ ሥርዓቱና በሰፊው አበሉ ላይ በ፺፭ አንቀጽ የተከፈሉ ክሶችና ውቅሶች አቅርቧል ። ከነዚህም ዋናዎቹ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ገርምሮ በንስሐ ሰጭነት በነፍስ አባትነት ሥርየተ ኃጢአት በመስጠት ከሕዝብ የምትቀበለውን ከፍ ያለ ሀብት በጥብቅ ተቃውሟል ። በዚሁ በ፲፭፻፺፭ ዓ. ም. የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን ፲ኛ በመልእክት ስለመሸፈቱና ስለአቀረባቸው ክሶች ቢያወግዙት የተወገዘበትን የመልእክት ወረቀት (BULLE PONTIFICALE) በዊንተንበርግ (ጀርመን) እደባባይ አቃጥሎ ትግሉን በጽሑፍና በስብከት ይቀጥል ዠመር ።

አሳቡ በዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ይልቁንም በጳውሎስ መልእክት የተደገፈ በመሆኑ ክርክሩን የጀርመንና የነምሳ መሳፍንት እየገባቸው ስለደገፉት ምንም ካቶሊክ ቢሆኑ በዚህ ጉዳይ ገዠቱ ፤ አስወጡ ፤ ያዙ ፤ እሰሩ እየተባለ ከሮማ የሚመጣውን የሊቀ ጳጳስ ትእዛዝ መሳፍንቱና ባለሥልጣኖቹ ንጉሠ ነገሥቱ ሻርል ፭ኛ ጭምር እምቢ ሰላሉ በነገሩ ሲመከርበት ሲዘከርበት ቆይቶ ጉዳዩ እያደር በእንግሊ

(1) ጎንዛሎ አንዳንድ ጊዜ ጎንዛሎስ ወይም ጎንዛሌስ ይባላል ።

ዝም አገር በየትም ደጋፊ እያገኘ ስለሄደ በመጨረሻ ቀሌምንጦስ ፯ኛ በጀርመን የሉተር ፣ በስዊስና በፈረንሳዊ አገር የካልቪን ክስና ውቅስ ስለአስገዳደቸው የቀሩትን የየአገሩን ጳጳሳትና ኢጲስ ቆጶሳት ሰብስበው የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳደር አውቀው ለማሻሻል ብዙ ጊዜ ስብሰባ እያደረጉ ከደከሙ በኋላ ሞቱ ።

ከርሳቸው ቀጥለው የተሾሙትም ጳውሎስ ፫ኛ በዚሁ መስመር የቤተ ክርስቲያኑን ነዋሪ አቅዋም ለማጽደቅ ፣ ሊሻሻል የሚገባውን መጥፎ ልማድ ለማሻሻል የክርስቲያኖቹ ነገሥታትና መሣፍንት የሚተባበሩትን ዘዴ በጉባኤ (ሲኖዶስ) ለማጥናት በትራንት (ኢጣልያ) ከ፲፭፻፵፭ - ፲፭፻፵፯ ዓ. ም. ድረስ በየጊዜው ቢሰበሰቡም በቅድሚያ ስለሚታየው ጉዳይ ስለ ስብሰባው ሥፍራ ጳጳሱ ጳውሎስ ፫ኛና የጀርመኑ ንጉሥ ሻርል ፭ኛ እየተከራከሩ ምንም የታወቀ ውሳኔ ሳይሰጡ በመካከሉ ጳውሎስ በ፲፭፻፵፱ ዓ. ም. እንደ አው. ቀ. ሞተው በርሳቸው እግር ካርዲናል ዣን ማሪ ቲዎኪ ዴል ሞንቲ የሚባሉት በ፲፭፻፶ ዓ. ም. ዩልዮስ ፫ኛ ተብለው በመንበረ ጴጥሮስ ተቀመጡ (1) ።

ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ቤርሙዴዝ ከኢትዮጵያ ወደ ሊስቦን ሂዶ ከመመለሱ በፊት የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛና የሮማው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስለኢትዮጵያ በመልእክት መመካከር ያዙ ። መቼም ከዚህ በፊት እንዳልነው እንደ አው. ቆጥር በ፲፭፻፴፯ ዓ.ም. የተላኩት አልቫሬዝና ጺጋ ዘአብ እየተሳሳቱም ለመወደድም እያሉ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ወደ ካቶሊክ መቅረብ እያስፋፉ ለንጉሡም ለጳጳሱም ነግረዋል ፣ ነገሥታቱ ልብነ ድንግልም ገላውዴዎስም በወረራና በመከራ ሰዓት ችግር እያስገደዳቸው የጻፉትን ደብዳቤ በማንበብና መሠረት በማድረግ የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማው ጳጳስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ወደ ካቶሊክነት ለማግባት መንገዱ ሁሉ በደንብ የተጠረገ ቀላል ጉዳና እንደሆነ አምነውበታል ። ከኬልቄዶን ጉባኤ ዠምሮ የተመሠረተውን በኢትዮጵያ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ ያለውን ውስጣዊ ጥላቻና ንቀት በዚህ ጊዜ ዘርዝሮ ለሁለቱም ያስረዳቸው ያለ አይመስልም ። በመጠኑ አልቫሬዝ ይልቁንም ዮሐንስ ቤርሙዴዝ አስረድተው እንደሆነ በዚህ አሁን በደረሰው ወረራና በተለገሠው የወታደር እርዳታ የተነሣ ነዋሪው ጥላቻ ፩ ጊዜ ለዘለቄታ የተሠረዘ እድርገው የቆጠሩት ይመስላል ።

የኢትዮጵያና የእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ከኬልቄዶን ጉባኤ (፬፻፶፩ ዓ.ም.) ወዲህ የተለዩ መሆናቸውን ፤ በዚሁ ምክንያት "Hérétiques schismatiques መናፍቅ በራሳቸው የተወገዙ" እየተባሉ ሲሰደቡ መኖራቸውንም ባይስቱት ከንግሥት እሌኒ ፣ ካፄ ልብነ ድንግልና ከዓፄ ገላውዴዎስ መልእክት ወዲህ እነዚህ የኢትዮጵያ የሸፈቱ መናፍቃን በሠሩት የመለየት ኃጢአት ተጸጽተው ወደ ሮማ ቤተ ክርስቲያን ሕጽን ተመለሱ የሚል እምነት ተጥሏል ። በተለይ ወደዚህ እምነት ሊጥላቸው የሚችለው የመጨረሻው ያፄ ገላውዴዎስ "አ አቡነ ጳውሎስ ሰማዕኩ ዘወሀብከነ ዮሐንስ አንበርኖ ውስተ መንበረ ጵጵስና" የሚለው ደብዳቤ ነው ።

(1) Histoire des papes-F. Hayward. ምዕ. 1-111 ገጽ 296 - 322

ISIC

ይህ ደብዳቤ ደርሷቸው የግዕዝኛው ቃል በትክክል ወደ ላቲን ወይም ወደ ኢጣልያ ተተርጉሞላቸው እንደሆነ በእርግጥ በኢትዮጵያና በንጉሡ ካቶሊክነት ለመተማመ ንና ጳጳስ ለመላክ እውነተኛ መንገድ አላቸው ። ቀጥሎ ከመስቀል ጦርነት ወዲህ የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣን በዓለም እየገነነ መሄዱ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ከዓረ ቦች ወረራ ወዲህ እየደከመ መሄዱ የበለጠ ሁኔታውን እያስተማመነው ሄደ ል ።

በቤርሙዴዝና በዓፄ ገላውዴዎስ መካከል የተነሣውን ጠብ ንጉሡ ደኸን ደብዳቤ ለመጻፍ የተገደዱት ከግራኝ ሞት በፊት ቤርሙዴዝ ወታደሮቹን ይገዩ እመለሳለሁ ብሎ በአስፈራራበት ምክንያት ብቻ መሆኑንም ሊገነዘቡት አይች ሉም ። ስለዚህ የሮማ ጳጳስና የፖርቱጋሉ ንጉሥ ተመካክረው ገና ቤርሙዴዝ ከኢ ትዮጵያ ወዳገሩ ሳይመለስ እርሱን እንዳልተሾመ ወይም የኢትዮጵያ ንጉሥ ቢሾመ ውም ሰውዬው ያለው መንፈሳዊ ትምህርትና የቤተ ክህነት አስተዳደግ ለዚህ የጵ ጵስና ደረጃ የማያበቃው ነው በማለት ሌላ በርሱ ፈንታ የተማረና ደረጃው ከፍ ያለ ሰው መርጠው ለመላክ በመልእክት ይመካከሩ ዠመር ።

በዚህ ጊዜ ኢኛሲዮ ደ ሎዮላ የሚባሉ መነኩሴ በ፲፭፻፴፬ በሞንማርትር (ፓሪስ) የመሠረቱት የኢየሱሳውያን ማኅበር ማኅበሩ በ፲፭፻፵ ዓ. ም. በጳጳሱ በጳ ውሎስ ፫ኛ በሕጋዊ ደንብ ጸድቆ በ፲፭፻፵፩ ዓ. ም. እኚሁ ኢኛሲዮ የበላይ መሪና አስተዳዳሪ ሆነዋል (1) ።የኢየሱሳውያን ማኅበር ዓላማው ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ታማኝ ሆኖ አዲስ በተሻሻለ መንፈሳዊ ትምህርትና ሥነ ሥርዓት በየአገሩ በተለይ ከአውሮፓ ውጭ አዲስ ቅኝ በሆኑ የአፍሪካና የእስያ የአሚሪካ አገሮች እየ ተበታተኑ በጥሩ አነጋገር በመስበክና በማስተማር ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ማፍራት ነው ።

ISIC

ስለዚህ ወደ ኢትዮጵያ ስለሚላከው ጳጳስ በፖርቱጋል ንጉሥና በሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት መካከል የአሳብ ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ ራሳቸው ዋናው የኢየ ሱሳውያን ማኅበር መሪ ኢኛሲዮ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እያስተማሩ ማሳመንን እንደ አንድ ቅዱስ የሐዋርያነት መልእክት በመቁጠር እኔ ልሂድ ብለው በጥብቅ ለሮማው ሊቀ ጳጳስ ለዩልዮስ ፫ኛ አመለከቱ ። ነገር ግን እንተን የመሰለ ሰው ከዚያ ከሩቅ አገር ይልቅ በዚሁ በአውሮፓ በብዙ ታገለግላለህ ። ይሁን እንጂ ወደ ኢትዮ ጵያ የሚላኩት ቀሳውስት ካንተው ከኢየሱሳውያን ማኅበር ተመልምለው ይላኩ የሚል ተስፋ ሰጧቸው ።

ስለዚህ ለዋናው የመልክተኞች ጓድ መሪ (ፓትሪያርክ) እንደ አሳሽ ወይም እንደ መንገድ ጠራጊ ሆኖ ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው ጎንዛሎ ሮድሪግ የሚባ ለው የዚሁ የኢየሱሳውያን ማኅበር አባል በቅድሚያ ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ ተልኮ እንደ አው. ቆ. በ፲፭፻፵፯ ዓ. ም. ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። እርሱም እንደመጣ ነገሩ ሁሉ በቀላል የሚፈጸምና በነቀፋ የሚረታ መስሎት በሮማ የሉተር ወገኖች የርሱን የካቶሊኩን ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት እንደሚነቅፉበት መቼም ኢትዮጵያው

(1) በኢጣልያ ቋንቋ አጠራር IGNAZIO በኛ በግዕዙ አጠራር አግናጥዮስ እንለዋለን ።

ያኑ በዚያን ሰዓት እያውቁም በማለት ሰሞኑን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የሚነቅፍ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን የሚያወድስ ጽሑፍ ሲያዘጋጅ ሰንብቶ በመጨረሻ በጉባኤ እንዲታይ አደረገ ።

በጉባኤው ላይ አዲስ የመጡት ግብጻዊው ጳጳስና ዓፄ ገላውዴዎስ በተቀመጡበት ጎንዛሎ ያዘጋጀውን ጽሑፍ ለንጉሡ ቢያቀርብ ጳጳሱ አትቀበለው ብለው ነበር ይባላል ። የሆነ ሆኖ በንጉሡ ፈቃድ ጽሑፉ ባደባባይ ተነቧል ። ካቀረባቸው ነቀፋዎች ውስጥ ፩ኛ በኒቅያ ጉባኤ የተሻረውን ቅዳሜን ታከብራላችሁ ፤ ፪ኛ በሐዲስ የተሻረውን ግዝረትን ታደርጋላችሁ ፤ ፫ኛ የአሳማ ሥጋ መብላት ያስኰንናል ትላላችሁ የሚል አለበት (1) ።

ንጉሡም ለዚህ ለአመጣው ነቀፌታ ሁሉ የሚገባ መልስ እየሰጡ በሰጡት መልስ መደነቁንና አንዳንድ ጊዜ ንጉሡ ለሚያመጡት ክርክር መልስ ያጣ እንደነበረ አለመሸሸጉን ላክሮዝ ባሳተመው መጽሐፉ ላይ እንደዚህ ሲል ጠቅሶታል ። ጎንዛሎስ ሮድሪግ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ የተቀበሉት ጊዜ ነገሩን ሁሉ ተስፋ አድርጎ እንደጠበቀው ሳይሆን አገኘው ። ከሮማ ቤተ ክርስቲያን የመደረብ ምንም ፍላጐት እንደሌላቸው ተገንዝበ ይኸንኑ አስታውቋል ። በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ከሌሎቹ ጋር እንደዚሁም በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሚከራከርበት ጊዜ ይኸው መስፍን (2) ኃይለኛና ብልህ ተከራካሪ መሆኑን ብዙ ጊዜም የሚመልስ ሰው እያጣ እንደተደናገረው ጎንዛሎ ራሱ አምኗል (3) ።

ISIC

የሆነ ሆኖ ዋናው ክርክር ወደፊት ዋናዎቹ እነ እንድርያስ ኢቪዮዶ ሲመጡ የሆነውን ከተመለከትን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ገላውዴዎስ ስለዚህ ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጉዳይ ፩ ጊዜ ለዘለቄታ የሰጡትን መልስ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እናነባለን ።

(1) Histoire du Christ. ገጽ 269 - 271 ። Histoire d'Abissinie - Yones E Monroe ገጽ 120 -121 ። Etudes sur l'histoire d'Ethiopie-René-Basset ገጽ 156 ፤ ቁ. 192 ። Storia della letteratura etiopica-Ignazio Guidi. ገጽ 71 - 72

(2) ገላውዴዎስን ማለቱ ነው ፤

(3) Hist. du Christianisme-La croze. ገጽ 272 - 273

## ምዕራፍ ፻፴፩

### የእንድርያስ አቪዬዶ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (እንደ አው. ቍጥር ፲፭፻፶፯ ዓ. ም. መጋቢት) የገላውዴዎስ ንጉሣዊ ኃላፊነት በሁለት ተከራካሪዎች መካከል ።

ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው ጎንዛሎ እንደ አው. ቍጥር በ፲፭፻፶፭ ዓ. ም. መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ተዋውቆ በሃይማኖት ሲከራከር እንደኖረ በሁለተኛው ዓመት በ፲፭፻፶፯ ዓ. ም. የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዩልዮስ ፫ኛና የኢየሱስ ማኅበር የበላይ አስተዳዳሪ ኢኛሲዮ ደ ሎዮላ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩትን አዘጋጁ ።

ቍጥራቸው የዋናዎቹ መልእክተኞች ፲፪ ነው ። ይኸም ሎዮላ ለንጉሡ እንደ ጻፈው ቍጥራቸውን ከ፲፪ ላይ መመደቡ በ፲፪ቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው (1) ። ከ፲፪ቱ የመሪመሪያዎቹ ሦስቱ ፤

፩ኛ. ዮሐንስ ኑኔዝ ባሬቶ ("Jean Nunez Barreto")

፪ኛ. ሜልኪዮር ካርኔይሮ ( "Melchior Carneiro" )

፫ኛ. እንድርያስ አቪዬዶ ( "André d'Oviedo" ) ይባላሉ ።

ከነዚህ የመሪመሪያዎቹ ሁለቱ የፖርቱጋል ተወላጆች ሲሆኑ ሦስተኛው አቪዬዶ የኤስፓኝ ተወላጅ ነው ። በቤተ ክህነት ሥልጣን ባሬቶ የሊስቦን ጳጳስ ፥ ካርኔይሮ የሂዮራፖሊስ (ቀድሞ ግሪክ አሁን ቱርክ) አቪዬዶ የኒቅያ "ቱርክ" ጳጳስ ተብለው የሦስቱም የሹመት ደረጃ ት[illegible]ል እንዲሆን ተደርጓል ። ይኸም ሹመት የተሰጣቸው ወደ ኢትዮጵያ ሊላኩ ሲሉ ለማክበርና በኢትዮጵያውያኑ ፊት ለማስከበር የተሰጣቸው የሹመት ደረጃ ነው እንጂ ቀድሞ የነበራቸው አይደለም ። ፫ቱም የተመረጡት ምናልባት አንዱ ቢሞት ሌሎቹ በየተራ እንዲተኩ ነው ይባላል ።

ከሦስቱ ደግሞ በመሪመሪያ ስሙ የተጠቀሰው ባሬቶ በዕድሜም ስለሚሸመግል ፤ የፖርቱጋል ዋና ከተማ የሊስቦን ጳጳስ ተብሎ ስለተሠየመ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ተብሎ ተሾሞ የበላይ አለቃ ሆነ ። በዚህ ዓይነት ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርበው ደብዳቤና ገጸ በረከት ከተዘጋጀላቸው በኋላ ግማሾቹ ከሊስቦን የቀሩት ከሮማ ተጠረቃቅመው ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት እንደለተመደ ወደ ሕንድ ከተማ ወደ ጎአ ሄዱ ። ወደዚያም ሲሄዱ የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ ለሕንዱ እንደራሴ ለፍራንቼስኮ ባሬቶ እነዚህን የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች በክበሬታ ተቀብሎ በ፭፻ ወታደር አሳጅቦ ወደ ኢትዮጵያ እንዲልካቸው አዞት ነበር ። ነገር ግን እንደ ራሴው ቍጥሩ እስከዚህ የሚደርስ ወታደር በዚህ ጊዜ ለዚህ ጉዳይ ስለሌለው በዚህም ላይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሮማ ቤተ ክርስቲያን የተሾመ ፓትሪያርክ ለመቀበል አይፈቅድም የሚሉ ወሬ በቅድሚያ ሰምቶ ነበርና በቀጥታ በተለይ ሽማግሌውን ባሬቶን መላክ ሥጋት ሆኖበት ሲመካከር በመካከሉ በምክር ባሬቶ ቀርቶ እንድርያስ አቪዬዶ አምስት የሚሆኑ ተከታዮች ይዞ ቢሄድ ይሻላል ተብሎ ተወ

(1) Hist. du Christ. ገጽ 271

ስኖ እንድርያስ አቪዬዶና አምስት የሚሆኑ ተከታዮቹ እንደ አው. ቀ. ፲፭፻፶፯ ዓ. ም. በመጋቢት ወር አርኪቆ ደረሱ ። ባሬቶም ኢትዮጵያን ሳያይ እዚያው ጐአ (ሕንድ) ሞተ ። አርኪቆ በአገር ተወላጅ አጠራር እስከዛሬ ድሆኖ ይባላል ። የድሆኖ ወደብ ከምጥዋ ወደ ደቡብ ምዕራብ ፲፫ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ነው ።

ከአርኪቆ ተጉዘው ደባርዋ በደረሱ ጊዜ ከዚህ በፊት እነ ክርስቶፎሮስ ደጋማን ተቀብሎ ያስተናገደው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አሁንም በዚሁ ሹመቱ ላይ ስላለ በመልካም ተቀበላቸው ። በደባርዋ ሳሉ አቪዬዶ የመልእክተኞቹ መሪ በባሬቶ ምትክ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ስለተባለ በዚሁ ሥልጣኑ ለዓፄ ገላውዴዎስ ደብዳቤ ጽፎ ደባርዋ መግባቱን አስታወቀ (1) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ምንም እንኳን ባለፉት ዓመቶች ቤርሙዴዝ በክርክር ቢያስመርራቸው ጎንዛሎስ የሚባለውም በሚያመጣው ክርክር ባያስደስታቸው ለሚያመጣው ክርክር ተገቢ የሆነ መልስ እየሰጡ በጠቅላላው ከግራኝ አህመድ ወረራ ለመገላገል የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማ ጳጳስ የሠሩላቸውን የወታደር ርዳታ ስለሚያውቁ አቪዬዶን ከነተከታዮቹ አስመጥተው በመልካም አቀባበል ተቀበሉዋቸው (2) ።

በአቀባበሉና በመስተንግዶው ረገድ አንዳች የሚቸግር ነገር የለም ። ችግርን የሚፈጥረው ቤርሙዴዝ ይጣላበት በነበረው መንገድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ታዛዥ ትሁን ፤ ጳጳስ ከእስክንድርያ ከመንበረ ማርቆስ መቀበላችሁን ትታችሁ ከሮማ ከመንበረ ጴጥሮስ ተቀበሉ ለዚያውም እነሆ እኔ ራሴ ለኢትዮጵያ የመዝመሪያው ጳጳስ ሆኜ ተሾሜ መጥቻለሁና ተቀበሉኝ ሲል ነው ።

በዚህ ጊዜ በንጉሡ ነገሥቱ ላይ ያለውን ችግር ለመገመት ቀላል ነው ። በፊት ከእስላሞች ጋር በአሁኑ ጊዜ ደግሞ አዲስ ከጋሎች ጋር ያላቸው የጦርነት ደመና እየከበዳቸው ከዚያም ለመውጫ የነዚህን የፈረንጆች ርዳታ ለማግኘት ሲሉ ወደ ነርሱ ሲያዘነብሉ ግብፃዊው ጳጳስ ከሊቃውንቱ ከነአባ ዝክሬ ከነ አባ ጳውሊ ጋር ቄርሎስ አትናቴዎስ የመሠረቷትን ዲዮስቆሮስ የተደበደበባትን ያያት የቅድም አያቱን ተዋሕዶ ሃይማኖት ከድቶ በልዮን ልጆች ሃይማኖት በሁለት ባሕርይ ሊገባ ነው ይሉዋቸዋል ። ከጎንዛሌስ ጋር ከሁለት ዓመት በፊት በጉባኤ ክርክር ሲደረግ ይህ ሰውዬ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ወደ ግዕዝ የተተረጐመ የነቀፋ ጽሑፍ አቅርቦላቸው ሊመለከቱ ሲፈልጉ ግብፃዊ ጳጳስ ይኸን እጉል የተነቀፍንበትን ጽሑፍ አታንብብ እስከ ማለት መድረሳቸውን አንብበናል ።

(1) ከድሆኖ ወዲህ ደባርዋ የባሕር ነጋሽ ከተማ የነበረ አሁን ካሰመራ ከተማ ፴ ኪሎ ሜትር ርቆ በምዕራብ በኩል የሚገኝ ነው ። እነክርስቶፎሮስ ደጋማ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር የተገናኙት በዚህ ከተማ መሆኑን እንባቢ ያስታውሰዋል ።

(2) Hist. du Christianisme............. ገጽ 273 - 275 Hist. de l'abissinie-Jones Monroe. ገጽ 120 - 123

እንደዚሁም ከባላቸውም ከልጆቻቸውም ጋር ሆነው ያን ሁሉ መከራ የተቀበሉት የቆሰለው ደጋማ በዓይነ ርግባቸው ወይም በቀጸላቸው የታሠረው በቤርሙዴዝ ፊት ተንበርክከው በማልቀስ ቤርሙዴዝንና ገላውዴዎስን ስሚን ሳሉ ያስታረቁት እናትዮዋ ሰብለ ወንጌል በአሁኑ ሰዓት ከሊቃውንቱ ጋር ሆነው ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዋና ጠበቃና ተከራካሪ ሆነዋል ። ንግሥቲቱን ለዚህ ተቃውሞ ያደረሳቸው ምናልባት ከፖርቱጋሎቹ ጋር ብዙ ጊዜ አብሮ በመቆየት ኑሮአቸውን ምናልባት የአሳማ ሥጋ ሳይቀር መብላታቸውን በማየት መጸየፍ ጭምር ይኖርበት ይሆናል (1) ። ለውጡንም ያስከተለው ይኸን የመሳሰለው የፈረንጆቹ አቅዋም ይሆናል ።

ባንድ ወገን ደግሞ ንጉሡ ወደ ወገኖቻቸው ወደ ተዋሕዶዎቹ ሲያዘነብሉ ፈረንጆቹ የኛ ጦር ደሙን አፍሶ የወደቀ መንግሥቱን አቁሞለት በዚሁ ውለታ ቀድሞም አባቱ አሁንም እርሱ ለሮማ ቤተ ክርስቲያን ለመታዘዝ ቃል የገባውን አሁን በመንግሥቱ ሲደላደል ጊዜ ክዶ ከግብፅ ጳጳስ አስመጣ እያሉ እንደሚያሟቸው ከሐሜታም አልፈው በቀጥታ እንደሚወቅሷቸው የታወቀ ነው ። በማናቸውም ረገድ አሁን ከእስክንድርያ ጳጳስ አስመጥተው በአጠገባቸው በአስቀመጡበት ሰዓት አቪዬዶን ተሾሞ እንደመጣ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክነቱን እሺ ብለው እንደማይቀበሉ የታወቀ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ታሪክ ነገሥቱ «ንጉሡ የፈረንጆቹን ሃይማኖት ወዶ እንድርያስን ፓትሪያርክ ብሎ ሾመው በኋላ ግን ሕዝቡ እንደ ግራኝ ጊዜ ያለ ሁከት እንዳያመጣበት ስለፈራ በእስክንድርያ ሃይማኖት ቆመ ። በዚህም ፈረንጆቹ አዘኑ» (2) ይላል ።

ታሪክ ነገሥቱ የተዘጋጀው የዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን ካለፈ በኋላ በጣም ቆይቶ ስለሆነ ጸሐፊው ወደኋላው ተመልሶ የዚህን ዘመን የሃይማኖት ጦርነት ሲተርክ በጠቅላላ በአጭሩ ከዚሀ በላይ የተመለከተውን ከመጥቀስ በቀር የቤርሙዴዝንና የእንድርያስ አቪዬዶን በምዕራፍ እየለየ በዝርዝር ቀንና ዓመተ ምሕረት እየጠቀሰ አላዘጋጀውም ። ምናልባት መጀመሪያው የፈረንጆቹን ሃይማኖት ወደው ከተቀበሉ በኋላ ሕዝቡ እንደ ግራኝ ጊዜ ሁከት እንዳይፈጥርባቸው በእስክንድርያ ሃይማኖት ቆሙ የሚለው የቤርሙዴዝን ሹመትና ለሮማ ሊቀ ጳጳስ ለጳውሎስ የጻፉትን ሲጠቅስ ይሆናል ። እርሱም ቢሆን ባለፈው እንደተመለከትነው የጦርነትና የፖለቲካ ጣጣ አስገድዷቸው ነው እንጂ አንድ ቀንም የፈረንጆቹን ሃይማኖት ከልባቸው ፈቅደው የተቀበሉበት ጊዜ የለም ።

ወይም በንጉሠ ነገሥትነት ኃላፊነታቸው የወቀሳው መጽሐፍ እንኳን ግብጻዊው ጳጳስና የቀሩት አይነበብ እያሉ ሲከላከሉ እርሳቸው ግን ተቀብለው ማንበባ

(1) Hist. du Christ. ገጽ 274

(2) ንጉሥሰ አፍቀረ ሃይማኖቶሙ ለአፍርንጅ ወሤሞ ለእንድርያስ (እንድሬያ አቪዬዶ) በትረያርክ ። ባሕቱ ፈርሃ ከመ ኢያምጽኡ ሕዝበ ኢትዮጵያ ሁከተ ላዕለ መንግሥቱ ከመ ዘመነ ግራኝ ወቆመ በሃይማኖተ እስክንድርያ ወበእንተዝ ኀዘኑ አፍርንጅ ፤ ታሪከ ነገሥት ገጽ 95 ።

ቸው ወይም እንዲነበብ ማድረጋቸው እንድርያስ አቪዬዶን ከነተከታዮቹ በደንብ ተቀብለው ማስተናገዳቸውን ከመሠረታዊው ከሃይማኖቱ አቀባበል ሳይለይ ጾሐፊው የነዚያን ሃይማኖት በመዠመሪያ የተቀበሉና በመጨረሻ አሳባቸውን የለወጡ መስሎት ይሆናል ። ሁለቱ ጉዳይ በዛሬ ዘመን አስተሳሰባችን ልዩ ነው ። በዚያን ዘመን ግን የካቶሊክ ሃይማኖት ያለውን ሰው ተቀብሎ ማስተናገዱ ሃይማኖቱን እንጂ ለወጠ ብሎ የሚያሳማበት ዘመን እንደነበረ የታወቀ ነው ። ሁኔታውም እስከ ዘመናችን ደርሷል ።

## ምዕራፍ ፻፵፪

### ከእንድርያስ አቪዬዶ የቀረበው የሃይማኖትና የልማድ ክርክር — ከዓፄ ገላውዴዎስ የተሰጠው የመጨረሻ መልስ (፲፰፻፵፭ ዓ. ም. ሰኔ ወር)

የሮማ የቄሣር ግዛት ካንድነት ተፋልሶ የምዕራብና የምሥራቅ የቄሣር ግዛት ተብሎ ከተከፈለ በኋላ የምዕራቡ በአረመኔዎች ወረራ ተውጦ ሲመነምን የምሥራቁ ከትልቁ ቆስጠንጢኖስ (፬ኛ መቶ ዓ. ም.) ዠምሮ ገናንነቱን ክብሩን ሳይነጠቅ ቱርኮች በ፲፭ኛው [illegible] ዓመተ ምሕረት ላይ እስኪደመስሱት ድረስ ኖረ ። በዚያን ጊዜ የቍስጥንጥንያውና የእስክንድርያው የፓትሪያርኮች መቀመጫ በዚያው በቄሣሮቹ ደጋፊነት አልወደቀም ነበር ። መቼም ፓትሪያርኮችና መንበራቸው የሚከበረው ቄሣሮቹ ራሳቸው ሲከብሩና ሲያከብሩት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ የቍስጥንጥንያ መንግሥት በቱርክ ከተደመሰሰ በኋላ የቍስጥንጥንያው መንበረ ዮሐንስ ተዳክሟል ። ቀድሞውኑ በ፩ና በ፪ ባሕርይ መከፈል ከግማሾቹ የቍስጥንጥንያ ነገሥታት ጋር ሲጣላ የኖረው የእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ ከ፯ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ዠምሮ በበኩሉ ዓረቦችና ግብፆች በአሁኑም ሰዓት ቱርኮች ያገሪቱ ገዥዎች ስለሆኑ ፈጽሞ ተዳክሟል ። ፓትሪያርኩ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ ወደ ኢየሩሳሌም መልከተኛ ሲልኩ ፈትም ከዓረቦቹ አሁንም ከቱርኮቹ ፓሻ (አገረ ገዥ) ፈቃድ እየጠየቁ በታላቅ ደጅ ጥናት ነው ።

እነዚህ ሁለት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መናብርት በደከሙበት ሰዓት የሮማው የጴጥሮስ ሊቀ መንበር በርሱም ላይ የሚሾመው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሥልጣኑም ክብሩም እየገነነ ከመሄድ ያላቋረጠው በተለይ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የበለጠ ገናና ነው ። ለመግነን ያደረሰው የርሱ የንስሐ ወይም የሃይማኖት ልጆቹ ይኸውም ማለት የርሱን ካቶሊካዊ ሃይማኖት የሚከተሉት የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ሻርል ፭ኛ የፈረንሳዊ ንጉሥ ፍራንሷ ፩ኛ ፤ የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ የእንግሊዝ ንጉሥ ሔንሪ ፰ኛ (በሚስት ፍቺ ከመጣላቱ በፊት) እነዚህ ሁሉ ራሳቸው እየገነኑ የሚያምኑበትን የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያንና እንደ መንፈሳዊ አባት ጳጳሱን ስለሚደግፉት ነው ።

በምዕራፍ ፹፯ ላይ የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ፫ኛ ከዓፄ ልብነ ድንግል የተላ ከውን አልቫሬጽንና ገጸ በረከቱን ሲልክለት ለርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ ለቀሌምንጦስ ፯ኛ የላከውን ደብዳቤ ብናስታውስ ነገሥታቱ ፓፓውን እንደምን እንደሚያከብ ሩት እንረዳለን ። በዚህ ደብዳቤ ላይ በተለይ የምንረዳው ንጉሡ ዮሐንስ ቀድሞ አባትየው አማኑኤል በተለመው ትልም ተመርቶ ወታደሮቼን እስከ ሕንድ ድረስ እየላክሁ የአረመኔዎችን አገር እያስገበርሁ ኢትዮጵያም ምንም ክርስቲያን ብት ሆን ወደ ሮማ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ሥልጣንዎ ሥር እንዲመጡ አድርጌያቸዋ ለሁ ሲል በነገሩ ተመክቶበታል ። ሊቀ ጳጳሱም ይኸንኑ በማመን በዚህም ላይ ከዓፄ ልብነ ድንግል ዘንድ የተላከው አልቫሬጽ በዝርዝር እያብራራ ስለአረጋገጠላቸው ቀጥሎም ያዔ ገላውዴዎስ የታዛዥነት ደብዳቤ ስለተከተለ የሮማ ሊቀ ጳጳስ ዩል ዮስ ፫ኛ እነ እንድርያስ አቪዬዶን ለኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ብሎ ለመላክ ምክንያት ሆናቸው ። ከነ እንድርያስ አቪዬዶ ቀደም ብሎ እንደ አሳሽ ወይም እንደ መንገድ ጠራጊ ሆኖ የመጣው ሮድሪጎ ጐንዛሎ (ወይም ጐንዛሊስ) ምንም እንኳን ሰውዬው በልስላሴም በዘዴም ወዳጅነትን ከማሳየት ጋር በዚያው ጐን በኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ላይ ጉድለት መስሎ የታየውን ባለፈው ያነበብነውን አቅርቦ ባደባባይ ቢከ ራከር ለሚያመጣው ክርክር ደንበኛ መልስ ከመቀበል በቀር እንደተመኘው እውነ ትሀ ነው የሚለው አልተገኘም ።

እነ እንድርያስ አቪዬዶ ከመጡ ወዲህም ንጉሡና መኳንንቱ ከሊቃውንቱ ጋር የእንድርያስ አቪዬዶን የኢትዮጵያ በትረ[SIC]ፓትርያርክነቱን ስለአልተቀበሉት አቪዬ ዶና ተከታዮቹ ስለ ጵጵስናው ሥልጣን እንደ ቤርሙዴዝ ክርር አድርጎ መከራከ ርን ተወት አድርገው በኬልቄዶን ጉባዔ እንዲዮስቆሮስ ተረቱ የተባሉበትን የክርስ ቶስን ሁለት ባሕርይ ለማጽደቅ የሮማ ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት ልዮን እውነት አለው ዲዮ ስቆሮስ አንድ ባሕርይ በማለቱ ተሳስቷል የሚለውን የቆየ ክርክራቸውን አመጡ ። ከዚህም ጋር ከሁለት ዓመት በፊት ሮድሪግ ጎንዛሌስ በሐዲስ የተሻረውን ግዝረት ታዘወትራላችሁ ፤ በኒቅያ ጉባዔ በቅዳሜ ፈንታ እሑድ ብቻ እንዲከበር የታዘዘ ውን ትታችሁ እንደ አይሁድ ቅዳሜን ታከብራላችሁ ፤ ክርስቶስ ከአፍ ወደ ሆድ የገባ አያስኰንንም ያለውን ረስታችሁ አሳማ የበላ ይኰነናል ትላላችሁ የሚለውን ወቀሳና ክስ ጨምረው በግዕዝ አስተርጉመው በጉባዔ ሲከራከሩበት ሰነበቱ ።

የክርክሩን ሁኔታ ታሪከ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ባጭሩ ጠቅሶ ያለፈውን በሌላ ቦታ እንደዚህ የሚል አለ ። «ገላውዴዎስ በነገሠ በ፲፪ኛው ዓመት ወንድ የሚባሉ የያፌት ልጆች የተወሰነላቸውን ባሕር አልፈው መጡ ። የፈረንጅ ጳጳስም ወደ ንጉሡ አደባባይ መጣ . . . . . አመጣጡም ከእስክንድርያ የመጣችውን ቀናችዪ ቱን ሃይማኖት ለማስነወር ፤ ከሮም የመጣችውን ጠማማዪቱን ሃይማኖት በግልጽ እየተናገረ ለማሞገስ ነው ። ሲያሞግስም እግዚአብሔር ለጴጥሮስ በፊቱ ካሉት ደገ ጊያዎች ልጆች ለማስነሣት መቻሉን ሳያውቅ አባታችን ጴጥሮስ ነው እያለ ይመ ካል ። በዚህ ዘመን የነበረው ንጉሥ ገላውዴዎስ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሆኖ ስለ ሃይማኖታቸው ጉድለት እየተከራከረ ከሊቃውንት ከነቢያትና ከሐዋርያት

የተጸፈውን ሰብስቦ እያቀረበ በመመለስ ያሳፍራቸው ነበር ።

በፊቱ እነሱ መርቅያንን ሲያመሰግኑ እርሱ ደግሞ ቴዎዶስዮስንና ስብስትያኖስን ያመሰግናል ። እነርሱ ልዮንን ሲያሞግሱ እርሱ ዲዮስቆሮስን ያሞግሳል ። እነርሱ በጴጥሮስ መንበር ሲመኩ እርሱ ጌታ በነበረበት በደብረ ዘይት በተሰቀለበትና በተቀበረበት እነዚህም የተቀደሱ ሥፍራዎች የሳባ የኖባ የኢትዮጵያ መምህር የሆነው የማርቆስ መንበር ባለበት በሆነው በእጁ በሆነው ይመካ ነበር« (1) ።

የግራኝ ወረራ ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን እንደ አጋጣሚ ደርሶ እኝህ ንጉሥ በተለይ ሥልጣን ከጨበጡበት ወዲህ ያለው የመንግሥታቸው አብዛኛው ዘመናቸው ያለፈው በመከራና በጸጸት ጥላ ውስጥ ነው ። ልጃቸው ዓፄ ገላውዴዎስ ደግሞ ግራኝን በመጣል የወደቀውን መንግሥት አንሥቶ ለማቋቋም የታደሉ ቢሆንም ይኸው ዕድላቸው በሃይማኖት ክርክር ፤ ከእስላምና ከጋላ ጋር በየጊዜው በሚደረግ ጦርነት የተከበበ ነው ። በሃይማኖትና በጦርነት የነበረባቸውን ሁለት ችግሮች ታሪክ ነገሥቱ ከዚህ በላይ አሳይቶናል ። ፫ኛም በምጥዋ በኩል ቱርኮች መጥተው ኤርትራን ስለወረሩ በኝህ ንጉሥ ላይ በችግር ላይ ችግር እንደተፈጠረባቸው ይታያል ።

በሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና በፖርቱጋል ንጉሥ ፈቃድ ተሾሞ የመጣው እንድርያስ አቪዬዶ ከላይ በተመለከትነው ዓይነት ከእስክንድርያ በአባ አትናቴዎስ ዘመን ጵጵስና አባ ሰላማ ፍሬምናጦስ በአክሱም የተከላትን የተዋሕዶ ሃይማኖት ለማስነወር የነቀፌታውን አሳብ በጽሑፍ አቅርቦ ለነበረው ንጉሡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ከነቢያትና ከሐዋርያት ከሊቃውንትም መጻሕፍት ጥቅስ እየጠቀሱ መልስ መስጠታቸውን ታሪከ ነገሥቱ በሚያመለክትበት ጊዜ በዚሁ ጐን ከቱርኮችና ከጋሎች ጋር የሚያደርጉትን የጦርነት ትግል በተጨማሪ ያወሳል ።

በክርክሩ ጊዜ አቪዬዶና ወገኖቹ የኬልቄዶንን ጉባዔ የመራውንና አንድ ባሕርዮችን ያስረታውን የቊስጥንጥንያን ንጉሥ መርቅያንን (2) ደብዳቤ ልኮ በመመስከር ለሁለት ባሕርዮች የረዳውን የሮማን ጳጳስ ልዮንን ሲያመሰግኑ ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስና ወገኖቻቸው በዚሁ ክርክር ተረታሁ ተብሎ ታሥሮ የሞተውን ዲዮስቆሮስንና ለአንድ ባሕርዮች በኤፌሶን ጉባዔ እየረዱ ሁለት ባሕርዮችን ያስረቱትን የቊስጥንጥንያን ነገሥታት እነ ዳግማዊ ቴዎዶስዮስን ማመስገናቸው እነዚያ የጴ

(1) አመ፲ወ፪ቱ ለመተ መንግሥቱ ለንጉሥ ክቡር ገላውዴዎስ ወጽአ መንገለ ምድረ ኢትዮጵያ (አቪዬዶ) ወእርጉ እምባሕር ደቂቀ ያፌት . . . . , ጳጳሲ ዘአፍርንጅ በጽሐ ኃበ ትዕይንተ ንጉሥ ምጽኢቱሰ ኮነ ለእንውሮ ሃይማኖት ርትዕት ዘተፈነወት ኢትዮጵያ እም እስክንድርያ ወከመ ያግህድ ወይወድስ ለሃይማኖቱ ጠዋይት ዘሠረፀት እምሮምያ እንዘ ይትሜካህ በብሂለ አቡነ ጴጥሮስ . . . . . . . ታሪከ ነገሥት ገጽ 108 ።

(2) የዚህ ንጉሥ ስሙ በኛ በግዕዙ መርቃያን ሲባል በላቲን Marcianus በፈረንሳዊ Marcien ነው ።

ጥሮስ መንበር በሆነው በሮማ ቤተ ክርስቲያን ሲመኩ እነዚህ የኛዎቹ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ መመካታቸውን የማርቆስ መንበር ከሊቀ ሐዋርያው ከጴጥሮስ አነስ ቢልም መንበሩን ከመካነ ቅዱሳኑ ጋር በማያያዝ መመካታቸውን ያመለክታል ።

የሆነ ሆኖ ክርክሩ ጥያቄውና መልሱ ብዙ ጊዜ ከፈጀ በኋላ አቪዩዶና ወገኖቹ ስለ ክርስቶስ ባሕርይና ስለኬልቄዶኑ ጉባዔ በተለይ ደግሞ ቅዳሚን በማክበር በግዝረት የእሣማ ሥጋ ባለመብላት የአይሁድን ሥርዓት ትከተላላችሁ ብሎ ላመጣው ክስ ሁሉ መደምደሚያ ደንበኛ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ መልስ ተሰጠው ። የተሰጠውም መልስ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው በመሠረቱ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት በኒቅያ ጉባዔ የወሰኑት ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኑ ጸሎት ሆኖ ከሚነበበው ከጸሎተ ሃይማኖት ጋር ይመሳሰላል ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥታት እሥራኤላውያን ፣ ወሃይማኖተ መርዔትየ እለ ሀለዉ በዐፀደ መንግሥትየ ።

ንሕነ ነአምን በ፩ዱ አምላክ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ ቃሉ ወውእቱ ኃይሉ ። ውእቱ ምክሩ ወውእቱ ጥበቡ ። ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወበደኀሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየአርቅ እመንበረ መለኮቱ ። ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እም ቅድስት ድንግል ። ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በ፴ ክረምት ወኮነ ብእሴ ፍጹመ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ በሳልስት ዕለት ። ወእምዝ በ፵ ዓለት ዓርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ። ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልበ ማህለቅት ለመንግሥቱ ። ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሰረፀ እምአብ ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ። ወንሤፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለም ። አሜን ።

ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዮን ወኢናጸንን ኢ ለየማን ወኢ ለጸጋም እምትምህርተ አበዊነ ፲ወ፪ ሐዋርያት ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ፣ ወ፸ወ፪ አርድእት ወ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት ዘተጋብኡ በኒቅያ ፻ወ፶ በቍስጥንጥንያ ወ፪፻ በኤፌሶን ።

ከመዝ ፣ ወከመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ ።

ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አኮ ዘናከብራ ከመ አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ እስመ እሙንቱሰ አይሁድ ኢይቀድሑ ማየ ወኢያነድዱ እሳተ ወኢያበስሉ ጸብሐ ወኢየሐብዙ ኅብስተ ወኢይትፈለሱ እምቤት ውስተ ቤት ።

ወባሕቱ ንሕነሰ ናከብራ እንዘ ነዓርግ ባቲ ቍርባነ ወንገብር ባቲ ምሳሐ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ ። አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ እሑድ እንተ ይእቲ ዕለተ ሐዲስ ዘይቤ ዳዊት በእንቲአሃ ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፈሣሕ ወንትሐሰይ ባቲ ። እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ፣ ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ ። ወባቲ ይመጽእ ዳግመ ለዕሤተ ጻድቃን ወለፍዳ ኃጥአን ።

ወበእንተ ሥርዓተ ግዝረትኒ አኮ ዘንትገዘር ከመ አይሁድ እስመ ንሕነ ነአምር ቃለ ምህሮሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘይቤ ተገዝሮሂ ኢይበቍዕ ወኢተገዝሮሂ ኢያሠልጥ

ዘእንበለ ዳእሙ ሐዳስ ፍጥረት ዘውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ ዘሂ ነሥአ ግዝረተ ኢይንሣእ ቊልፈተ ። ኵሉ መጽሐፈ ትምህርት ለጳውሎስ ሀለወ ሀቤነ ወይሜህረነ በእንተ ግዝረት ወበእንተ ቊልፈት ። ወባሕቱ ግዝረትሰ ዘኮነ በኀቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥንተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወኖባ ። ወከመ ስቁረት እዝን ዘሰብአ ሕንድ ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በአቂቦ ሕገ ኦሪት ዳእሙ በልማደ ሰብእ ።

ወበእንተ በሊዓ ሐራውያን አኮ ዘንትከላእ በዓቂበ ሕገገ ኦሪት ከመ አይሁድ ለዘኒ በልዐ ኢናስቆርሮ ወኢናረኩሶ ወለዘኒ ኢበልዓ ከመ ይብላዕ ኢናከብሮ ። በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል ዘኒ በልዐ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ ወለኵሎሙ እግዚአብሔር ተወክፎሙ ። መንግሥተ እግዚአብሔር ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን ወእኩይሰ ለሰብእ በሊዕ ምስለ እቅፍት ። ወማቴዎስ ወንጌላዊ ይቤ አልቦ ዘያክል አርኩሶቶ ለሰብእ ለእንበለ ዘይወጽእ እምአፉሁ ። ወዘሰ ውስተ ከርሥ ይበውእ ወይትገመር ጽመ ወይትገደፍ ወይትከዓው ወያነጽሕ ኵሎ መባልዕት ወበብሂለ ዝንቱ ቃሉ ነስተ ኵሎ ሕንፃ ስሕተቶሙ ለአይሁድ እለ ተምሀሩ እመጽሐፈ ኦሪት ።

ሊተሰ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለ ይሜህሩ በትእዛዝየ በዐጸደ መንግሥትየ ወኢይትገኀሡ እምፍኖተ ወንጌል ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማን ወኢለጸጋም ። ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሎ በመጽሐፈ ዚአነ እስመ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ አዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለኵሎሙ እለ ተጠምቁ አይሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወባሕቱ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትኄረም እምበሊዓ ሥጋ እንስሳ ዘያፈቅር ሥጋ አሣ ወቦ ዘያፈቅር በሊዐ ሥጋ ዶርሆ ወቦ ዘይትኄረም እምበሊዓ ሥጋ በግዕ ወኵሎ ዘከመ አደመ ልቡ ይተሉ ። ከመዝ ውእቱ ስምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ በእንተ መብልዓ ሥጋ እንስሳ አልቦ ሕግ ወአልቦ ቀኖና ውስተ መጽሐፈ ሐዳስ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን ። ወጳውሎስኒ ይቤ ገብረ የአምን ኵሎ ለይብላዕ ።

ዘንተ ኩሉ ዘጽሑፍ ለጽሑፍ ከመ ታእምር ጽድቀ ሃይማኖትየ ። ተጽሕፈ በ፲ወ ፰፻ በ፶ወ፰ ዓመት እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ፳ወ፪ ለሰኔ (1) በሀገረ ዳሞት (2)» ።

በዚህ የእምነት ማስታወቂያ በመገናኛ መሪያዎቹ መስመሮች በአጭሩ የክርስቶስን የሕይወት ታሪክ በኒቅያ ጉባዔ የተወሰነውን ጠቅሰው ቀጥለው ፲፪ቱ ሐዋርያትና ጳውሎስ ፸፪ቱ አርድእት ፤ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት በኒቅያ ፤ ፻፶ው ሊቃውንት በቊስጥንጥንያ ፪፻ ሊቃውንት በኤፌሶን ከወሰኑት ግራም ቀኝም አንልም ሲሉ አረጋግጠው ፮፻፴፮ ሊቃውንት የተካፈሉበትን ፩ ባሕርይና ተዋሕዶ ሃይማኖት የተወነጀለበትን ፪ ባሕርይ የታወጀበትን አራተኛውን የኬልቄዶኑን ጉባዔ በፍጹም ውድቅ አድርገውታል ።

በዚህ ግልጽ ማስታወቂያ ምንም የማያከራክረውን ራሷ የሮማ ቤተ ክርስቲያን የምታምንበትን ፫ቱ የኒቅያ የቊስጥንጥንያ የኤፌሶን ጉባዔ የወሰኑትን ብቻ እቀበላለሁ ሲሉ በመጨረሻው በኤፌሶን ጉባኤ በቅዱስ ቄርሎስ መሪነት የክርስ

(1) ዓፄ ገላውዴዎስ በ፲፰፻፶፮ ዓ. ም. ስለሞቱ የተጻፈው እንደ አው. ቀ. ፲፰፻፶፰ ጎንዛሌስ የመጣበት ዓመት ነው ይህ ክርክር መልስ የሰጠበት ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ፲፰፻፵፱ ዓ. ም. መሆን አለበት ።

(2) Historiam Aethiopicam Commentarius-Jobi Ludolfi No. XXIX. ገጽ 237 - 241 ።

ቶስ ፩ አካል ፩ ባሕርይ የጸደቀበት ስለሆነ ከዚህ እምነት አልነቃነቅም ብለው ሲዘጉ ባንድ ወገን ጠላቶቻቸው ሊከራከሩዋቸው የማይችሉትን አቅዋም ጨብጠ ዋል ማለት ነው ።

ክርክር ላለማብዛት እንግዶችን ፈጽሞ ላለማሳዘን ራሱን የኬልቄዶኑን ጉባዔ በዝምታ ውስጥ እንዳለፉት እንደዚሁ ልዮንንም መርቅያንንም ፍላቭያኖስንም የሚነቅፍ ዲዮስቆሮስንም የሚያሞግስ ዓረፍተ ነገር አላገቡም ። ይኸም የጽሑፍ ውሳኔ በብዙ ቀን ጥናትና በዘዴ እንደተዘጋጀ ያስታውቃል ።

ቡተረፈ ከእምነቱ ክርክር አልፎ ስለ እሳማው ሥጋ አለመብላት ስለቅዳ ሚው መከበርና ስለግዝረት የኢትዮጵያንና የሕዝቡን ልማድ ለማስነወር ያመጣ ውን ከዚህ እንደሚከተለው ደህና አድርገው በዝርዝር መልሰዋል ።

፩ኛ. በሐዲስ የተሻረውን ቅዳሜን እንደ አይሁድ ታከብራላችሁ ላለው እሥራኤላ ውያን ከግብፅ በወጡበት ሰዓት በሙሴ አማካይነት ሕግ ሲቀበሉ ፯ኛዪቱን ቀን ቅዳሜን እንዲያከብሩ በኦሪት መታዘዙ እርግጥ ነው (1) ። በዚሀ ምክን ያት አይሁድ በዚህ ቀን ፈጽሞ ምንም ሥራ አይሠሩም ። ዛሬም አድቬንቲ ስት የሚባለው የአሜሪካኖች ቤተ ክርስቲያን ኦሪትን ለመሻር አልመጣሁም የሚለውን መሠረት በማድረግ ቅዳሜን ያከብራሉ (2) ። ይሁን እንጂ የቀ ረው የካቶሊክ ፤ የኦርቶዶክስ ፤ የተዋሕዶ ፤ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲ ያናት በቅዳሜ ፈንታ እሑድን ያከብራሉ ። ይኸንንም የሚያከብሩት በኒቅያ ISIC ጉባዔ (፬ኛው መቶ ዓ. ም.) ሦስቱ መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ጌታችን ሞቶ የተነሣበት እሑድ በቅዳሜ ፈንታ እንዲከበር የደነገጉትን ሕግ በመከ ተል ነው ።

ነገር ግን ባዔ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (፲፬፻፳፮ - ፲፬፻፷) የዲድስ ቅልያን መጽሐፍ በመከተል በእሑድ ዋዜማ ያለው ቅዳሜም እንደ ሁለተኛ ሰንበት እንዲከበር አዘው የነበረው በዚህም ባዔ ገላውዴዎስ ዘመን ይከበር ኖሮ ሮድሪግ ኮንዛሌስና እንድርያስ ኦቪዬዶ ይኸንኑ እንደነውር አድርገው በጽሑፍ ወቅሰው ለነበረው ንጉሡ መልስ ሲሰጡ «ቅዳሚን ጌታን እንደሰቀ ሉት እንደ አይሁድ አናከብራትም ። . . . . . አይሁድ በዚች ቀን ውሀ አይቀ ዱም ፤ እሳት አያነዱም ፤ ዳቦ አይጋግሩም ፤ ወጥም አይሠሩ ከቤት ወደ ቤት (ወደ ጐረቤት) አይዘዋወሩም ። እኛ ግን በዚች ቀን ቁርባን እናቀርብባታለን ምሳም እየበላን እናከብራታለን ይኸውም ሐዋርያት በዲድስቅልያ መጽሐፍ ያዘዙትን በመከተል ነው ። የምናከብራትም በክርስትና ከታደሰንባት ከእ ሑድ ጋር እኩል አድርገን አይደለም . . . . . ብለው መልስ ሰጥተዋል (3) ።

፪ኛ. እንደ አይሁድ ትገረዛላችሁ ያለው ይኸውም እንደ ቅዳሜ በኦሪት በተጻፈው

(1) ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 31 ቍ. 13 - 18 ። ምዕ. 35 ቍ. 2
(2) ማቴዎስ ምዕ. ቍ. 17
(3) ዘፍጥረት ምዕ. 17 ቍ. 11 - 14 ። ዘሌዋውያን ምዕ. 12 ቍ. 3

መሠረት የእስራኤል ወንድ ልጅ ሁሉ በተወለደ በ፰ኛው ቀን ይገረዛል ። ይኸም የኦሪት ልማድ ወደኛ ዘንድ ዘልቆ የክርስቲያን ልጅ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ እንደ አይሁድ ልጅ በተወለደ በ፰ኛው ቀን ግዝረትን እንደቀጠለ ነው ። የአውሮፓ ክርስቲያን ግን ቀድሞም አረማዊ በነበረበት ጊዜ ይኸን ግዝረት አያውቅም ። በክርስትናም ጊዜ በግሪክና በሮማ ክርስትናን ያስተማረው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆረንቶስ ሰዎች በጻፈው በመዠመሪያዪቱ መልእክት ግዝረትም አለመገዘርም ዋጋ የለውም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ ነው . . . . . . የተገረዘም ወደቆላፍነት አይመለስ ሳይገረዝ የተጠራ ክርስቲያን የሆነ አይገዘር ስላለ ትተውታል (1) ።

ለዚህ ወቀሳ ንጉሡ መልስ ሲሰጡ ጳውሎስ እላይ ያዘዘውን በሙሉ በመጥቀስና በማመን «እኛ የምንገዘረው እንደ አይሁድ አይደለም . . . . ነገር ግን እምነት ሳይሆን ከአገር ልማድ ጋር የተያያዘ ነው ። የኖባና (ሱዳን) የኢትዮጵያ ሰዎች ፊታቸውን ወይም ጉንጫቸውን እንደሚበጡ ወይም ሕንዶች ጆሮአቸውን እንደሚወጉ የኛም ባገር ልማድ ምክንያት ይገረዛሉ እንጂ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለው አይደለም» ሲሉ መልሰዋል ።

፫ኛ. የአሳማ ሥጋ አትበሉም ፤ መብላትም ነውር ነው ትላላችሁ ብሎ ላቀረበው ወቀሳ የዚህን ጉዳይ በኦሪት አሳማ (እርያ) ስኮናው የተሰነጠቀ ቢሆንም እያመሰኳምና ርኩስ[illegible]ላችሁ የሚል ትእዛዝ አለ (2) ። ነገር ግን ጌታችን በወንጌል ወደ አፍ የገባ ሰውን አያረክሰውም ስላለ (3) የአውሮፓ ክርስቲያኖች ለሰውነታቸው የሚስማማ ከሆነ ሁሉንም ይበላሉ ። በዚሁ መሠረት እናንተ ግን አትበሉም ላለው መልስ «የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ስንል አይደለም የማንበላው ነገር ግን ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ እንደገለጸው የሚበሉትን አንንቅም በማይበሉትም አንፈርድም . . . . . የእግዚአብሔር መንግሥት መብል መጠጥ አይደለም» ሲሉ መልስ ሰጥተው ሰው ሁሉ ልቡ የፈቀደውን መብላት እንደሚችል ዘርዝረው በዚሁ ክርክሩ ተዘጋ (4) ።

እንድርያስ ኦቪዬዶ የወቀሳውን ጽሑፍ ያቀረበው ቀድሞ በኢትዮጵያ ከነበሩት ከነአልቫሬጽ ከነኮቪልሃን ከነጎንዛሌስ እየተማከረ እንደሚሆን እንደዚሁም ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ገላውዴዎስ ምንም እንኳን በስማቸው ጽሑፉ ቢዘጋጅ ራሳቸው የተማሩ ብልህ ተከራካሪ ቢሆኑም አስቀድሞ ጉዳዩ የተከለ ሃይማኖትን መልክ በደረሱት በእጨጌ ዮሐንስና በእጨጌ እንባቆም ምሑር በሆነውና በጦር ሠራዊቱ አለቃ በአፈወ ድንግል ፤ በነአባ ዝክሬ በነአባ ጳውሎስ ተመክሮ የተዘጋጀ መሆን አለበት ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሳልተማሩትና ዓለም ለሠለጠነበት እነርሱ ሳልተ

(1) ቆሮንቶስ ፩ኛ ምዕ. 7 ቍ. 18 - 19
(2) ዘሌዋውያን ምዕ. 11 ቍ. 7
(3) ማቴዎስ ምዕ. 15 ቍ. 11 -20
(4) የሮሜ መልእክት ምዕ. 14 ቍ. 2 - 17

ማሩት ለማቲማቲክ ፤ ለሲያንስ ለደረቅ ታሪክ ዕውቀት ይቸገሩ እንደሆን ነው እንጂ በብሉይና በሐዲስ በሊቃውንት መጻሕፍት ውስጥ ላለ ዕውቀትና ታሪክ ላተ ራረኩና ለሐተታ አሰጣጡ እንኳን በጽሑፍ በቃልም ለመከራከር በቂ ችሎታ አላ ቸው ። በተለይ በዚህ የሃይማኖት ክርክር ጊዜ ከኛ ወገን የተጻፈው ታሪክ ነገሥት «ንጉሡ ገላውዴዎስ ከፈረንጆች ሊቃውንት ጋር ሆኖ እየተከራከረ በማሳፈር ይመ ልስላቸው ነበር.....» ያለው የወገን ጸሐፊ በተለምዶ ድጋፍ ያሰፈረው ነው እንዳ ይባል ከፈረንጆቹ ወገን ስለዚህ የሃይማኖት ክርክር የተጻፈው ሁሉ ይኸስ ይብዛ ይኸ ንኑ የሚያጸድቅ ነው ። እነርሱም ከርሳቸው የሚመጣው ጥያቄ አስቸጋሪ ለቀረበላ ቸው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ አጥጋቢ መሆኑን ያመለክቱ ነበር ።

ከዚህም ጋር ስለጠቅላላው አቀባበላቸውና ስለግል ጠባያቸው ማኑኤል ፈርና ንዴዝ የሚባለው ከጻፈው ላይ አልቤር ካሜረር ወደ ፈረንሳዊ ተርጉሞ ያቀረበው እንደዚህ የሚል ነው «......ንጉሡ በሰብአዊ መንገድና በፍቅር ተቀብሎን ከሰላ ምታው ልውውጥ በኋላ ያገረ ገኘው (የሕንዱ) ደብዳቤ ቀርቦለት ሲያነበው በሮማ ቤተ ክርስቲያን ሥር ሁኑ ከሚለው ላይ ሲደርስ አለመቀበሉን በቅያሜ ይገልጥ ነበር ። ነገር ግን በባሕርዩ ነፃ ፣ ቸርነትና ደግነት በሰውነቱ ስለሚታይ አክብሮቱን በፍጹም አላጐደለም ። ከእስላሞቹ ጋር ገና (ያልተለቀቀውን ለማስለቀቅ) ለመዋ ጋት በሚደራጅበት ጊዜ እንኳን መልክተኞቹን መከባከቡን አላቋረጠም ። ምንም እንኳን በፊተኛው ጊዜ (ለሮማ ቤተ ክርስቲያን) እታዘዛለሁ ብሎ የነበረውን አላ ቡን ቢለውጥም በኢትዮጵያ ግዛት እሱን የመብለ ብልህና ንጉሣዊ ጠባይ ያለው የለም ። የኤስፓኙ ተወላጅ ቄጡው (አንድሬያ አቪዬዶ) በቁጣ ቃል "አንተም አባ ትህም ለሮማ ቤተ ክርስቲያን እንታዘዛለን ብላችሁ አልነበረም?" ሲለው እርሱ ደግሞ በጽሞና እነጋገር "ስሕተት ነው በአሳብ አልተግባባንም..... ከእስክንድ ርያ ቤተ ክርስቲያን ርቀን የሮማ ቤተ ክርስቲያን ታዛዥ መሆን አይቻለንም" እያለ ይመልስ ነበር ሲል ከዚህም ሰፋ አድርጎ የኝህን ንጉሥ ባንድ ወገን ብርታታ ቸውን በሌላው ወገን ሰው አክባሪና ቀና መሆናቸውን ያሳያል (1) ።

(1) La Mer Rouge - première partie XVIème siècle le Chap. X. ገጽ 273 - 292 ።
Rerum Aethiopica rum Scrip....Vol. X.

## ምዕራፍ ፷፩

## ክርስትናን በሥፍራው ለመመለስና ለመጠበቅ የተዘጋጁት መጻሕፍትና ተመል ሰው የተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ።

ግራኝ አህመድ ንጉሡ ነገሥቱን በሽምብራ ኩሬ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ራስ እስላም ሰገ ድንና አዝማች ተክለ ኢየሱስን በአይፈርስ በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ራስ ወሰን ሰገድን ቁርቁራ ላይ (በዛሬው ቢሾፍቱ አጠገብ) በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. ድል ካደረገ ወዲህ የደ ቡቡ ክፍለ ክርስቲያን ሹማምንቱ በጦርነትም ላይ ከተማረኩ በኋላ ሲገደሉ የቀ ረው ሕዝብ በጅምላ እየተያዘ መስለሙን የሹማምንትና የመኳንንት ሚስቶች ከም ርኮ ላይ እየተነዱ ራሳቸው እየሰለሙ የእስላም ሚስትና ገረድ መሆናቸውን አንብ በናል ።

ንጉሡ ነገሥቱ ከሸዋ ወደ ቤተ አምሐራ ከዚያም ወደ ቤገምድር ወደ ጐጃም ወደ ትግሬ እየተሰደዱ በሄዱ ጊዜ እግር በእግር እየተከታተለ እነዚህን አውራጃ ዎች ሁሉ እንዳጠፋ አብያተ ክርስቲያናቱንና ገዳማቱን ሀብታቸውን በቅድሚያ እያዘረፈ ማቃጠሉን ሕዝቡን ማስለሙን በዝርዝር ያነበብነውን እንመለስበትም ።

ስለዚህ የርሱ ግዛት በጸናበት በተለይ ሰሜኑን ክፍል መውረር ከቻለበት አን ሥቶ እስከሞተበት ዓመት ድረስ (፲፭፻፳፩ - ፲፭፻፴፭ ዓ. ም.) ባለው አሥር ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ አውራጃዎች የተለመዱት የመስቀል ፤ የልደት ፤ የጥምቀት ፤ የቃና ዘገሊላ የፋሲካ የሕዝብ በዓላት ማኅሌት ተቁሞ ቅዳሴ ተቀድሶ በይፋ የተከበ ሩበት ቀን ያለ አይመስለኝም ።

ታሪከ ነገሥቱ «በዚህ ዘመን ብዙ ሕዝብ ከክርስትና ሃይማኖት ወደ እስላም ነት ተለወጠ ። ያልተለወጡት ክርስቲያኖች ከአሥር አንድ አይሆኑም» ያለውን እናስታውሳለን ። በዚህ ምክንያት አሁን ግራኝ ሲሞት ሁሉንም ከሥፍራው ለመ መለስ ብዙ ዝግጅትና ብዙ ለውጥ ያሻል ። የፈረሰ መንግሥት መልሶ ማቋቋም ብቻ ሳይሆን በእስልምና ሃይማኖት ባሕር ውስጥ ጠልቆ ብቅ ጥልቅ እያለ ሲዋኝ የቆየ ውን የክርስትና ሃይማኖት ከሥፍራው ለመመለስ ብዙ አድካሚ ነገር አለ ።

ከዚሁ ጋር የቀድሞው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ በ፲፭፻፳፪ ዓ. ም. ላይ አርፈው አሁን አዲሱ ጳጳስ አባ ዮሳብ እስከመጡበት እስከ ፲፭፻፵ ዓ. ም. ድረስ በ፲፰ ዓመት ውስጥ ከቀሳውስቱ ከካህናቱ ከዲከቆናቱ ውስጥ አብዛኞቹ ሰልመዋል ። ምናል ባት ከእስላሞቹ ፊት በመሸሽግ ያልሰለመ ቄስና ደብተራ እንዳለ በአሁኑ ሰዓት ያረጀል ዲያቆንም እንዳለ ወደ ሙሉ ሰውነት ይመጣል ።

ስለዚህ በ፲፰ ዓመት ውስጥ ክህነት ዲቁና ቅስና የሚሰጥ ጳጳስ በሌለበት ሰዓት ቀድሞ የተቀበሉት ግማሾቹ ስለሰለሙ የቀሩትም በእርጅና በሞት ስለሚጐ ድሉ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጊዜ ከታላቅ ችግር ላይ ወድቃ እንደነበረ በግልጽ ይታ ያል ። ካህናቱም ቀሳውስቱም ምዕመናኑም የግራኝ ሥልጣን በተዘረጋበት ሰዓት በግዴታ ስለሰለሙ እስላሞቹ ያሉትን እየፈጸምን በልባችን ሃይማኖታችንን እንጠ ብቃለን የሚሉ ቢኖሩም በግድ ከእስላሞቹ ጋር ሲኖሩ እስላሞቹ ያረዱትን እንበ

ላም ብለው እንደ ቀድሞው ተጸይፈው እምቢ ማለት አይችሉም ። ያለዚያ የሰይፍ በትርና ሞት ይከተላል ። በሌላው ጊዜ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብለው ባርከው ክርስቲያኖቹ ያረዱትን እስላሞቹ እንደማይበሉ እንደዚሁም "ቢስሚላሂ" ብለው እስላሞቹ ያረዱትን ክርስቲያኖቹ በፍጹም አይበሉም ። አሁን ግን በግዴታም ቢሆን ከሰለሙ በኋላ ከበሉ እንደሰለሙ ወይም እንደረከሱ መቆጠር አለባቸው ። በግዴታ መስለሙም መብላቱም ስላልቀረ ሁሉም ሃይማኖቱን እንዳረከሰው ስለተቆጠረ ምንም እንኳን አሁን ግራኝ ሞቶ የሰለመው ሁሉ ተመልሰናል ቢል ከሁሉ በፊት የቤተ ክርስቲያን ዓምድና መሠረት የሚሆኑትን የካህናቱን ጉዳይ ለማከናወን ዓፄ ገላውዴዎስ ባንድ ወገን ከቤርሙዴዝና ከአንድርያስ ኦቪዶ በሚከራከሩበት ጊዜ የመዠመሪያ ዋና ተግባር አድርገው የቆጠሩት ከእስክንድርያ ከማርቆስ ወንበር ጳጳስ ማስመጣት በመሆኑ አባ ዮሳብን ቀደም አድርገው አስመጡ (1) ።

ስለዚህ ጳጳሱ ከመጡ ወዲህ በመንፈሳዊ ሥልጣናቸው ክህነት ዲቁና ቅስና እየሰጡ ቤተ ክርስቲያን ታደሰች ። ቤርሙዴዝ እንደ መጣ ከርሱ ቅስናና ዲቁናም የተቀበለ እንዳለ ሁለት ባሕርይ ከሚል ጳጳስ የተሰጠው አይረጋም ተብሎ በዚህ ጊዜ እንደገና ሁለተኛ ከግብጻዊው ጳጳስ ሳያሳድስ የቀረ አይመስልም ።

ኢትዮጵያውያን ከመካከላቸው ጳጳስ አይሹሙ የሚለው ከእስክንድርያ ሊቃውንት ዘንድ የተዘጋጀው ፍትሐ ነገሥት ባያግድ ይኽንንም ሕግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እሺ ብላ በመቀበል ፈንታ አሁን በመጨረሻ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እንደሆነው ታዛዥነቷን ፤ ልጅነቷን ሳትለቅ ከሊቃውንቷ መካከል ጳጳስ ለማሾም ስምምነት ብታደርግና ፈቃድ ብታገኝ ኖሮ ይህ በጳጳስ ማስመጣት በኩል ያለው ችግር ሊቀነስ በቻለ ነበር ። ነገር ግን ይኽን የመሰለ አሳብና አስተያየት ፈቃድ መጠየቁም ማግኘቱም በዚያን ጊዜ በፍጹም የማይታሰብ ነው ።

የሆነ ሆኖ የመጡት ጳጳስ ዘራቸው ግብጻዊ ቋንቋቸው ዓረብኛ ከመሆኑ የተነሣ በቀጥታ ከሕዝቡና ከካህናቱ ጋር በዚያው በአባትነታቸው ስሚት ብቻ ካልሆነ በቀር ግዕዝ ወይም አማርኛ ስለማያውቁ የዓረብኛውን ቋንቋና መጽሐፉንም የኛዎቹ ስለማይረዱት በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ሁልጊዜ በቀጥታ በመሆን ፈንታ በአስተርጓሚነት አማካይ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ክህነት ለመስጠቱም ሆነ በተለይ ደግሞ እገሌ ስልሚል እገሌ እስላም ያረደውን ሲበላ ኖሯል የተባለውን ሁሉ ወደ ጥንቱ ሃይማኖቱና ልማዱ ለመመለስ የሚያስችል ልዩ ልዩ የሃይማኖትና የሥነ ሥርዓት መጻሕፍት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ እየተተረጐመ እየተደረሰም እንዲዘጋጅ አስፈለገ ።

ለነዚህ መጻሕፍት ዝግጅት ከሁሉ የበለጠ የደከሙ የቀድሞ ስማቸው ሰሊህ (ወይም ሰሊክ) የነበረው በኋላ እጨጌ እንባቆም የተባሉት ሊቅ ናቸው ። እርሳቸ

(1) ቤርሙዴዝ አባ ዮሴፍ ያላቸው ስሕተት ነው ። ታሪከ ነገሥት አባ ዮሳብ መሆናቸውን አረጋግጧል ገጽ 122

ውም ዘራቸው ዓረብ ሲሆን (1) ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በደብረ ሊባኖስ በምን ኩስና ሲኖሩ ባዬ ልብነ ድንግል ዘመን ላይ እንፍራንቼስኮ አልቫሬጽ ወደ ኢትዮ ጵያ በመጡበት ዓመት በ፲፭፻፲፪ (፲፭፻፳ እ. ኤ. ቍ.) የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ተብ ለው መሾማቸውን ከዚህ በፊት አንብበናል ።

እርሳቸውም አንቀጸ አሚን - የሃይማኖት በር የሚባለውን መጽሐፍ የደረሱ ናቸው ። እንባቆም ዓረብኛና ቁራን በትክክል ስለሚያውቁ በሚያውቁት መንገድ ሐዲስንና ቁራንን እያስተያዩ የክርስቲያን ሃይማኖት በእስላም ፊት ብልጫ አለው በማለት በግላቸው አስተያየት በዚሁ ጽሑፋቸው እየተነተኑ ጽፈዋል ።

በተለይ ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ እላይ እንዳመለከትነው በጅምላ የሰለ መው ፤ እስላም ያረደውን የበላው ከእስላም ወንድ የተገናኘችው ሴት ወይም ከእስ ላም ሴት የተገናኘው ክርስቲያን ሁሉ እንደረከሰ ተቆጥሮ ለነዚህ ሁሉ ወደነበረ የክርስትና ሃይማኖት መመለሻ የሚያገለግል አንድ መጽሐፍ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ተተርጕሞ ተዘጋጀ ። የመጽሐፉ ስም መጽሐፈ ቄድር ይባላል ። እርሱም ከመዠመ ሪያው ላይ በግዕዝ «ቀኖና መጽሐፈ ቄደር ዘአንበሩ መምህራን ቤተ ክርስቲያን በእንተ ዘክህደ ሃይማኖቶ አው እርከሰ ሥጋሁ ወዘመወ ምስለ ዘኢምዕመናት አው ተባዕት አው አንስት መነኰስ ወመነኮሳይት . . . . .» እያለ ይቀጥላል ።

ይህ መጽሐፍ በቄስ እጅ እየተደገመ ቄሱ በእብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደገና ሲያጠምቀው ሃይማኖቱን የለወጠው ወይም ከእስላም የተገናኘው እላይ ግዕዝኛው እንዳለው ሴት ብትሆን ወንድ የሴትም የወንድም መነኩሴ ቢሆን ከርክሰቱ ንጹሕ ሆኖ ወደ ፍጹም ክርስቲያንነቱ ይመለሳል ማለት ነው ።

እንደዚሁም ዓፄ ገላውዴዎስ ከሞቱ በኋላ መጽሐፈ ንስሐ የሚባለውን መጽ ሐፍ አንድ ስሙ ያልታወቀ በግብፅ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ተር ጕሞ የላከው መጽሐፍ ለዚሁ ሥራ አገልግሎት ላይ ውሏል (2) ።

በዚህ ምክንያት የቀድሞ አባቶች በተለይ በዚሁ የተዋሕዶ ሃይማኖት በተናጋ በት ሰዓት ባገርም ያሉት ካገር ውጭ በግብፅም አገር ያሉት የኢትዮጵያ ሊቃውንት እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ በፊት በቤርሙዴዝና በእንድርያስ እቪዶ ፊት የካቶ ሊክን ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣንና የበላይነት ልዩ ልዩ መጻሕፍት በመድረስ እን ደተቃወሙ አሁን ደግሞ በእስላሞቹ ፊት ይኸን የመሳሰለውን የሃይማኖት ማጽ ኂያ መጽሐፍ ከማዘጋጀት ጋር ነዋሪውን የተዋሕዶ ሃይማኖት መልሰው አቋቋሙ ።

ለእስላሞቹ መቃወሚያ አንቀጸ አሚን ፣ መጽሐፈ ቄድር ፣ መጽሐፈ ንስሐ ፣ እንደተዘጋጀ እንደዚሁም በየጊዜው የካቶሊክ ሃይማኖትን ለመቃወም ወይም ለመ ከራከሪያ ሃይማኖተ አበው መዝገበ ሃይማኖት ፍካሬ መለኮት ፀወነ ነፍስ ፤ ሐመረ ነፍስ ፤ መርስ አሚን ፤ መጽሐተ ልቡና የሚባሉት መጻሕፍት ግማሾቹ የተዋሕዶ ሃይማኖት መደበኛ ከሆነው ከእስክንድርያ ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ከዚያም ወደ አማ

(1) ቼሩሊ ከኢራክ የመጡ ሳይሆኑ አይቀሩም ብሏል La letteratura etiopica. ገጽ 126

(2) Storia della letteratura etiopica Ignazio guidi. ገጽ 72

ርኛ ሲተረጐሙ አብዛኞቹ ከሊቃውንቱ እእምሮ በቀጥታ የተጻፈሱ ናቸው ።
ዋናው መሠረታዊ የሆነው ሃይማኖተ አበው የሚባለውን የራስ አምዱ ልጅ መባጻዮን ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ሲተረጐመው የቀሩት ደግሞ እነዚሁ ኢየሱሳውያን በስብከት ሕዝቡን ወደ ካቶሊክ ለመሳብ በሚጣጣሩበት በነዘድንግል ፥ በነሱስንዮስ ጊዜ በ፲፮ኛውና በ፲፯ኛው መቶ ዓ' ም. የተዘጋጁ ናቸው ።

እነዚህ መጻሕፍት ባገራችን በያለበት ተበታትነው እንደሚገኙ የታወቀ ነው ። ነገር ግን ታትመው ለሕዝብ ስለአልተዳረሱ ወይም ካሉበት በማኅተም ዝርዝራቸው ስለአልወጣ ያሉበትን በትክክል ማወቁ ይቸግራል ።

ለዕውቀት የሚሽቀዳደሙት ፈረንጆች ግን ከኢትዮጵያ ወደየአገራቸው እየወሰዱ በየቤተ መጻሕፍቶቻቸው አስቀምጠዋቸዋል ። በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቍጥር ፩፻፲፱ ተሰጥቷቸው የተቀመጡበትን የፍካሬ መለኮትን ፥ የሐመረ ነፍስን ፥ የመርስ አሚንን ፥ የመዝገበ ሃይማኖትን ፥ የፀወነ ነፍስን ፥ የመጽሔተ ልቡናን የአሠርቱ ተስዕሎታትን ግልባጮች ሙሴ ኤንሪኮ ቼሩሊ አግኝተው ወደ ኢጣልያ እየተረጐሙ እንደ ኤ. ቍ. ፲፱፻፶፰ እና በ፲፱፻፷ ዓ. ም. በማኅተም አሳትመው አራብተዋቸዋል ።

በዚህ ዘመን እንደሌላው ዘመን አንዳንድ ጊዜ በሌላም አገር እንደሚደርሰው በኢትዮጵያ ላይ ባንድ ጊዜ ብዙ ችግር የገጠመበት ዘመን ነው ። የግራኝ ወረራና ያመጣው መከራ ወራሪው በመሞቱ ቢዘጋም እርሱ የከፈተው የወረራ ዘመን ሌሎቹን ችግሮች ሊወልድ ችሏል ። የጋላ ወረራ የተተካው ከርሱ ወረራ ቀጥሎ የርሱን ወረራ ተንተርሶ ነው ። ቤርሙዴዝ የቀሰቀሰው የሃይማኖት ጦርነት በርሱ የወረራ ሰበብ በእርዳታ ምክንያት ከፖርቱጋሎቹ የተፈጠረ ነው ።

የሆነ ሆኖ ወታደሩ የወታደርነት ሥራውን በየሥፍራው ሲፈጽም ካህናቱና መምህራኑ በበኩላቸው በጽሑፍም በእንደበትም ከካቶሊክም ከእስላምም ሲዋጉ ንጉሡ ነገሥቱ ገላውዴዎስ ሁለቱን ወገኖች አጣምረው ሁለቱንም የጦርነት ግንባር እየመሩ ጊዜያቸውንም ሕይወታቸውንም ለኢትዮጵያ ሲሰዉ ባለፈው ከተመለከትነው የበለጠ ወደፊት እናነባለን ።

ክርስትናን ለመመለስና ለማጥበቅ በሥነ ጽሑፍ ድርጅት በሚደክምበት ጊዜ በየአውራጃው ተቋቁሞ የነበረው የእስላሞቹ ድርጅት በሚፈርስበት ሰዓት የፈረሱትና የተቃጠሉት ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት እየተመለሱ እንዲሠሩ ማድረጉም አንድ ሌላ ራሱን የቻለ ተግባር ነው ። ባሁኑ ጊዜ ተመልሰው የተሠሩትን አብዛኞቹን በግራኝ ወረራ ሰዓት በምን አኳኋን እየተዘረፉ እንደተቃጠሉ እንብበናል ።

ተመልሰው የተሠሩትን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ያንዳንዶቹን ሥፍራቸውንና የባለታቦቱን ስም ባይገልጽ ታሪከ ነገሥቱ ዝርዝራቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ይሰጣል ።
የደብረ ብርሃን
የደብረ ሊባኖስ

የምስአለ ማርያም
የገነተ ጊዮርጊስ
የደብረ ሕንጸታ
የደብረ ድማኅ
የመካነ ሥላሴ
የወልደ ነጐድጓድ
የደብረ ኪሩቤል
የአትሮንሰ ማርያም
የኤንድሮስ ማርያም
የታዕካ መንግሥት
የደብረ ጽርሐ ማርያም
የገነተ ማርያም
የአባ ጊዮርጊስን (ዘጋሥጫ)
የደብረ ቤቴል
የእግዚአብሔር አብ
የደብረ እስጢፋኖስ
የመርጡለ ማርያም
የደብረ ዘይት
የናዝሬት
የአምበር ቂርቆስ
የገሊላ
የአጥሊላ
የደብረ መጊህ
የኅለተ ማርያም
የኅሐ ጽዮን
የደብረ ከርቤ
የደብረ ወርቅ

ISIC

## ምዕራፍ ፻፵፬

## የመሬትና የግዛት ጠብ በፖርቱጋልና በኢትዮጵያ መካከል ኖሯል ? — የፖርቱጋል በእስፓኝ መንግሥት መጠቅለል

አንድ ንጉሥ እንደ ዕድሉ በዘመኑ ባገር ላይ ጦርነት ሲመጣበት የሌላው ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ደግሞ የሰላም ዘመን ሊሆን ይችላል ። የሦስተኛው ንጉሥ ዘመን ደግሞ እንዳጋጣሚ ጦርነትና ሰላም የተቀላቀለበት ዘመን ይሆንበታል ። በኢትዮጵያ ምንም የጦርነት ችግር ሳይደርስበት ረዥም ዘመን መንግሥቱን በሙሉ በሰላም ያሳለፈ ንጉሥ አይገኝም ። ከውጭም ጠላት ባይፈጠር የቀረው ቢቀር አንድ ቀንደኛ ወይም አንድ ከእገሌ እወለዳለሁና ልንገሥ በማለት ከውስጥ ተነሥቶ የረጋውን መንግሥት ሲያደፈርስ በርሱም ሰበብ ከሁለት ወገን ሰላማዊ ሕዝብ ሳይቀር በብዛት ይሞታል ። እንዲያውም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከተደረገው ጦርነት ውስጥ በርከቶ የሚታየው የርስ በርሱ ጦርነት ነው ። ይኸንንም ሁኔታ የነገሥታቱ ልጆች ተሰብስበው እንደ አምባ ግሼን ባለው ተራራ ወይም እንደ ሐይቅ ባለው ደሴት መወሰናቸው ሊያግደው አልቻለም ።

በዚህ መካከል ያኄ ገላውዴዎስን ዘመነ መንግሥት ያሰብነው እንደሆነ ከሰላም ዘመንነት ምን ያህል እንደሚራራቅ እንመለከታለን ። እነሆ የሃይማኖቱ ክርክር ባለፈው በተሰጠው መልስ ቢዘጋም እንድርያስ አቪዬዶ እንደ ቤርሙዴዝ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ወይም ጳጳስ ነኝና እወቁኝ፤ወይም ተቀበሉኝ እንደ ጎንዛሎም የቤተ ክርስቲያናችሁ ሥነ ሥርዓትና ልማድ በሮማ ቤተ ክርስቲያን ዓይነት ይለወጥ ብሎ መከራከሩን ቢተውም ንጉሡም እርሱ ይህን ሲተው በአገሩ ላይ በሰላም እያስተማረ ለመኖር ቢፈቅዱለትም በዚሁ ጐን በደቡቡ ክፍል ባንድ ወገን ፈጽመው ያልተወገዱት እስላሞችና ባዲስ ጉልበት ከአፍሪካ ቀንድ ተቀስቅሰው የተነሡት ባሌን ያሁኑን አሩሲንና አካባቢውን የወረሩት ጋሎች በሌላ ወገን በሰሜን በኩል በምጥዋና በደሆኖ (አርኪቆ) በኩል እስከ ደባርዋ ድረስ ያለውን አውራጃ ሁሉ የወረሩት ቱርኮች አስቸግረዋቸዋል ። በዚህ ምክንያት ግዕዛዊው ታሪክ ነገሥት «ባንድ ወገን ከፈረንጆቹ ሊቃውንት ጋር ሲከራከር ባንድ ወገን ከቱርኮች ጋር በምን አኳኋን ለመዋጋት እንደሚችል ይመካከር ነበር» ሲል አውስቶታል (1)።

የሆነ ሆኖ አሁን በፖርቱጋሎቹ በኩል ጠበኛውና እልኸኛው ቤርሙዴዝ አባቡ ሳይከናወንለት ቀርቶ ወዳገሩ ከተመለሰ ወዲህ ቁጡው የእስፓኙ ተወላጅ እንድርያስ አቪዬዶ ከንጉሡ በተሰጠው ውልውል በሌለበት መልስ የሃይማኖቱ ጉዳይ ከተዘጋ ወዲህ ሌላ የታወቀ ጠብ በኢትዮጵያና በፖርቱጋሎቹ መካከል አል

(1) ወበውእቱ መዋዕል ሀለወ ውእቱ ንጉሥ ገላውዴዎስ ማዕከለ ፪ቱ ፈያት እምለፈ ይትዋሥአ ለማዕምራነ አፍርንጅ በእንተ ሕፀተ ሃይማኖቶሙ . . . . . ወእምካልእትሂ ለፈ ኮነ ሀልወ እንዘ ይመክር በዘ ይፅብዖሙ ለወንድ ዘሙእቶሙ ትርክ (ቱርክ) . . . . . ወያበትሕዎ በእንተ ዐቂበ እሀጉራት እምፀብእ ጋላ . . . . . ጉንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕላቸው ምዕ. 54 ገጽ 63 - 65 ።

ተነሣም ። ቤርሙዴዝ ባለበት ጊዜ ወይም ከተመለሰ በኋላ የፖርቱጋል ንጉሥ ባደረገው የወታደር እርዳታ ምክንያት ሰንደቅ ዓላማዬ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጐን ይሰቀል መሬትም ተከፍሎ ይሰጠኝ የሚል በገሀድ ያቀረበው ጥያቄ በሰነድ መልክ አላጋጠመኝም ።

ነገር ግን ክርስቶፎሮስ ደጋማ በግራኝ ተማርኮ ከመሞቱ በፊት በአንድ ወገን ከእስላም ወረራ ላድናችሁ መጣሁ ብሎ ለንግሥት ሰብለ ወንጌል ከገለጸ ወዲህ በአምባ ሠነይትና በሰፀርት ተዋግቶ የቀናው ጊዜ ደግሞ ፴ ማይል አገር በፖርቱጋል ንጉሥ ስም መያዙን ለወንድሙ ለእስጢፋኖስ ደጋማና ለንጉሡ ለዮሐንስ ፫ኛ ደብዳቤ መጻፉን ካስታንሆዞ ጠቅሷል ። ይኸም ከመጣ ወዲህ ያደረገውን ለማመልከት እንጂ የተያዘው አገር ለፖርቱጋል ንጉሥ ቅኝ አገር ይሆናል የሚል አሳብ ያለበት አይመስለኝም ። ለወንድሙና ለንጉሡ የጻፈው ሙሉው ራፖር ስለማይታወቅ አሳቡን በትክክል አናውቅም ። ዓፄ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለአማኑኤልና ለልጁ ለዮሐንስ በጻፉት ደብዳቤ ላይ በቀይ ባሕር አካባቢ ባሉት አገሮች የፖርቱጋል ወታደሮች ገብተው እየመሸጉ ቢይዙና ከእስላም ቢከላከሉ መንግሥቱ ስንቅ ይሰጣል የኔ ሰው ማናቸውንም ርዳታ ያቀርባል ያሉትን ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከክርስቶፎሮስ ደጋማ ጋር ደባርዋ ላይ ተገናኝተው ንግግር ሲለዋወጡ እነዚህ አገሮች የርሱ በመሆናቸው በርሱ አገሮች ዓይነት በመተዳደራቸው ውለታው ለፖርቱጋል ንጉሥ ይከፈ[illegible]ብለው በዚያው በጭንቁ ሰዓት የተናገሩት የባላቸውን የቆየ አሳብ በማጽደቅ ይኸንኑ ቱርክና ፖርቱጋል የሚሻሙትን አደገኛ ቀበሌ ከእስላሙ ከቱርኩ ክርስቲያን ፖርቱጋል ቢይዘው እንደተስማሙበት የማይካድ ነው ።

ታሪከ ነገሥቱ ባለፈው እንዳነበብነው ፈረንጆች (1) ከሮም በመጡ ጊዜ (2) በመሐላ ስለገቡት ውል በየአገሩ ደልድሎ አሰማራቸው ። ስለ ሃይማኖታቸው ግን ትልቅ ሁከትና ጠብ ክርክር ከነአባ ዝክሬ ጋር ተነሥቶ ሳለ ንጉሡ ከመዠሪያው ላይ የፈረንጆቹን ሃይማኖት ወዶ ሳለ በኋላ ሁከት እንዳይነሣበት በእስክንድርያ ሃይማኖት ቆመ ያለውን ከዚህ በፊት ሐተታ ስለሰጠንበት እንመለስበትም ።

ነገር ግን ሌላ ግዕዛዊ ጽሑፍ የኢትዮጵያን መሬት ከሦስት እጅ አንድ እጅ ለመስጠት በአጽናፍ ሰገድና በፈረንጆቹ ንጉሥ መካከል ታላቅ መሐላ ተደርጎ እንደነበረ ያወሳል (3) ። ጽሑፉን ያዘጋጀው ሰው ዓፄ ገላውዴዎስ (አጽናፍ ሰገድ) የኢትዮጵያን ሲሶ መሬት ለፖርቱጋል ንጉሥ የሰጡበትን የመሐላ ውል ከወዴት እንዳገኘው ስለማይገልጽ በራሴም በኩል ይኸን የመሰለ ውል ያደረጉበት ሰነድ ስለአልገጠመኝ ከሃይማኖቱ ጐን ስለዚህ ጉዳይ ምንም ሐተታ ለማድረግ አልቻ

(1) የተዋጉትን ፖርቱጋሎች

(2) ከሊስቦን ወይም ከሕንድ በማለት ፈንታ ሮም ያለው ስሕተት ነው ።

(3) ወበ እንተ ዘኮነ ዓቢይ መሐላ ማዕከለ አጽናፍ ሰገድ ወማዕከለ ንጉሠ አፍርንጅ ከመ የሀበ ሣልስተ እደ*ሃ* ለኢትዮጵያ ....... ብሎ ወደሌላ ጉዳይ ይተላለፋል ።

ልሁም ። ታሪክ ነገሥት ጸሐፊው ይኸን የመሰለውን በጽሑፍ ያሰፈረው አብዛኛ ጊዜ ካለበት ዘመን ወደ ኋላ ተመልሶ ወሬ እየጠየቀ የጻፈው ስለሆነ ምናልባት የቃል ንግግር ኖሮ ወይም በዘመኑ ተወርቶ የነበረውን ለማውሳት ብቻ ይሆናል ።

ቤርሙዴዝም ከርሱ ወገን የሆኑት ፖርቱጋሎችም ዋናው ሲታገሉበት የነበረው ክርክር ስለ ሃይማኖት ስለ ቤርሙዴዝ የጵጵስና ሥልጣን ሆኖ ስለሰንደቅ ዓላማ አያያዝ አንድ ቀን የተነሣውን ጠብ እንብበናል ። በዚህ ጊዜ ሁሉ አንድ ጊዜም የመሬትና የግዛት ጠብ አልተነሣም ። እነ እንድርያስ አቪዬዶ ሲመጡም ሁሉም የቤተ ክህነት ሰዎች ተመርጠው ስለሃይማኖት ጉዳይ መጡ እንጂ ከነርሱ ጋር ስለ መሬት ስለ ግዛት ወይም ስለ ፖለቲካ ሊነጋገር የመጣ የቤተ መንግሥት ሰው አልነበረባቸውም ።

ነገር ግን ከዶጋማ ጋር መጥተው ደማቸውን ለኢትዮጵያ አፍስሰው ከቤርሙዴዝ ጋር ተጣልተው ሳይመለሱ ከርሳቸው ጋር ለቀሩት ለሁሉም ፖርቱጊዞች ከሽልማቱ ከወርቁ ከፈረሱ ስጦታ በቀር በየአውራጃው ለምለም መሬት ርስትና ጉልት በምሪት እየተከሉ አስደስተዋቸዋል ። እነርሱም ከኢትዮጵያ ሴት ወይዛዝር እየተጋቡ ንጉሡን ሲያገለግሉ ኖረው ባገሪቱ ሕዝብ መካከል ተውጠው ቀርተዋል ። በአሁን ጊዜም ከነርሱ ዘር የወረዱ አልፎ አልፎ ይገኛሉ ።

የፖርቱጋል መንግሥትም በዚህ በመጨረሻው የዓፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ሲሶ መሬት ለመስጠት የመሐላ ውል ቢኖርም ባይኖርም በላከው የወታደር እርዳታ ምክንያት የኢትዮጵያ ሲሶ ይሰጠኝ ብሎ ለመከራከርም ለማስገደድም በሰፋፊው ግዛቱ የተነሣ ኃይሉ በያለበት ተበታትኖ አይችልም ነበር ። በዚህም ላይ በፊቱ ሁለት ታላላቅ እንቅፋቶች ስለገጠሙት የዚህን የኢትዮጵያን ጉዳይ ሊያስብበት አልቻለም ። ከታወቁት እንቅፋቶች ውስጥ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፤

፩ኛ. እነ እንድርያስ አቪዬዶ ወደ ኢትዮጵያ እንደ አ. ቆጥር በ፲፭፻፶፯ ዓ. ም. ከገቡ በኋላ ወዲያው የቱርክ መንግሥት የኤርትራን ወደብ ምጥዋን ይዞ የሌላ አገር ወታደር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ዘግቶታል (1) ።

፪ኛ. ይኸውም ዋነኛው ምክንያት በኢስፓኝ የዳግማዊ ፊልጶስ አነሣሥ ነው ። የኢስፓኝ ንጉሥ የፊልጶስ እናቱ የፖርቱጋል ንጉሥ የአማኑኤል ልጅ ኤልዛቤል የራሱ የዮሐንስ ፫ኛ እኅት ነች ። አባቱ ያ የታወቀው በጀርመንና በኢስፓኝ በነምሳና በስሜን በሆላንድና በዴንማርክ አገሮች ላይ ንጉሠ ነገሥት የሆነው ሻርል ፭ኛ ነው ። ከነዚህ ከሁለቱ በተለይ ከሻርል በመወለዱ የተነሣ እንደ አው. ቆጥር ከ፲፭፻፵፱ ዓ. ም. ዠምሮ ራሱ እየገነነ አጐቱን ዮሐንስ ፫ኛን እያቀዘቀዘ ሄደ ። አባቱ ሻርል ፭ኛ ዙፋኑን ለርሱ ተናዞ በ፲፭፻፶፭ ዓ.ም. መንግሥቱን ትቶ ወደ አንድ ገዳም መንና የሄደ ጊዜ ፊልጶስ ከኢስፓኝ ከናፖሊ ከሲሲል ከሳርዴኝ ግዛት ጋር ሆላንድን ጨምሮ ያዘ ። በደቡብ አሜሪካ በሰሜን አፍሪካ ሩቅ ምሥራቅ በስሙ ዛሬ ፊሊፒን እየተባለ የሚጠራውን

(1) Histoire de l'abissinie - Jenes Monroe. ገጽ 121

ሁሉ ይዞ በጠቅላላው የፖርቱጋልን መንግሥት ስለ አዳከመው በዚሁ ጊዜ ዮሐንስ ፫ኛ ይኸን የመሰለ የውስጥና የውጭ የአገዛዝና ያስተዳደር የፖለቲካ አመራር ስለአለበት በፍጹም የኢትዮጵያን ጉዳይ ለመተው ግዴታ ሆነበት ። እንዲያውም በመ ጨረሻ በሚቀጥለው ጊዜ በ፲፭፻፹ ዓ. ም. ላይ ይኸው ዳግማዊ ፊልጶስ የናቴ የኤልዛቤል አገር ነው በማለት ራሱን ፖርቱጋልን ስለጠቀለለው ስለ ኢትዮጵያ አሳቢ ሚሲዮን ላኪም ኤስፓኝ ሆነ ። ስለዚህ በሚቀጥለው ዘመን ይኸውም ማለት ባዔ ሚናስና ባዔ ሠርፀ ድንግል ጊዜ የኢትዮጵያ ግንኙነት ከፖርቱጋል ጋር መሆኑ ቀርቶ ከኤስፓኝ መንግሥት ጋር ሆነ ።

ነገር ግን እውቆም ይሁን ወይም በችግር ምክንያት የኢትዮጵያን ሲሶ መንግሥት ሳይጠይቅ በዚህ ምክንያትም ፖርቱጋል የራሱንም አገር ወታደር የኛንም ሰው ደም ሳያፋስስ ነገሩ በዚሁ ዓይነት ስለተዘጋ በፊተኛው ግራኝ አህመድን በመጣል ረገድ በተደረገው ጦርነት የልጆቹ የነክርስቶፎሮስ ደጋማ ደም ስለ ፈሰሰ ኢትዮጵያ በዛሬው ዘመን በሞዛምቢክና በአንጎላ ነፃነትና ጠብ መካከል ምንም እንኳን ከሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች ጋር በኅብረት ከዚህ መንግሥት ጋር በፖለቲካ የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነቷን ብትቆርጥም በጠቅላላው የዚህን መንግሥት ውለታ ፈጽማ መርሣት የለባትም ።

ISIC

# ክፍል ፯

# ያፄ ገላውዴዎስ ትግልና የሕይወታቸው ፍጻሜ

## ምዕራፍ ፻፵፰

## የአቤቶ ሚናስ በመሐመድ ተለውጦ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት (፲፭፻፴፰ ዓ. ም.)

በምዕራፍ ፺፰ የአቤቶ ሚናስን መማረክ በምዕራፍ ፻፲፱ ላይ ወደ ዘቢድ ባሻ መላኩን በዝርዝር ያነበብነው ትዝ ይለናል ። የተማረከው በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ግንቦት ፳፫ ቀን ሲሆን ወደ ዘቢድ ባሻ ግራኝ የላከው በሰሀርት ጦርነት ቆስሎ በሸሸበት ዓመት በ፲፭፻፴፱ ዓ. ም. ስለሆነ ምንም ወሩ በትክክል ባይታወቅ ጦርነቱ የተደረገው በዚሁ ዓመት መጋቢት ፳፱ ቀን ስለሆነ ወደ ዘቢድ የተላከበት ወር ሚያዝያ ከዚያም ቢዘገይ ግንቦት መሆን አለበት ። ስለዚህ ሚናስ ወደ ዘቢድ ከመላኩ በፊት በግራኝ አህመድ እጅ ፫ ዓመት ያህል ጊዜ ቆይቶ ከዚያ ወደ ዘቢድ በረሃውን በግመል ባሕሩን በመርከብ ከሌሎቹ ምርኮኞች ጋር ተጉዞ ደርሷል ማለት ነው (1) ።

ወደ ዘቢድ ሲላክ ሁለቱም ላዕከ ማርያም ተብለው ባንድ ስም የሚጠሩት እንዚያ የተሰለቡት የሁለት እትማማች ልጆችና ሌሎችም ብዙ አብረው አሉ ። ሁለቱ ላዕከ ማርያም ያፄ ናዖድ ልጆች የዓፄ ልብነ ድንግል እኅቶች የእሙተ ድንግልና የሮማን ወርቅ ልጆች ናቸው ። በተለይ ስለ ሮማን ወርቅ ልጅ በሐምሌ ፳፩ ቀን የሚ፳፩) ላዕከ ማርያም የሮማን ወርቅ ልጅ ሞተ ። አባቱ የገኝ ንጉሥ ሣሞ ወልድ ይባል (2) . . . . . . ላዕከ ማርያም ተማርኮ ከይማም (ግራኝ) ፊት በቀረበበት ጊዜ በአክብሮት ተቀብሎት ሳለ ከእስላም ሃይማኖት ጋር በመተባበር ፈንታ የወገኖቹን መከራና ሞት እያየ ማዘኑንና ማልቀሱን ስለተመለከተ እንዲሰለብ አዘዘ ። ከዚያም ወደ ቱርኮች ንጉሥ (ዘቢድ ባሻ) እንዲላክ አዘዘ ። በጉዞም ጊዜ በግመል ቁልቁል እያንጠለጠሉ በረሃብና ውኃ ጥም እየተሰቃየ የመን ደረሰ ። በዚያም ባሻው ከሞተ ወዲህ ወዳገሩ ተመልሶ ቤተ ክርስቲያን በማሠራት ለደሀ በመመጽወት ኖረ . . . . የሞቱ ጊዜ ሲደርስ ወንዶችና ሴት ባሮቹን ከመገዛት ነፃ አውጥቶ ሞተ» ። ስለሁለተኛው ላዕከ ማርያም ግን ምንም አይናገርም ። የሆነ ሆኖ እንደ ታሪክ ነገሥቱ አጻጻፍ የዘቢድ ባሻ የንጉሡን ልጅ አቤቶ ሚናስን ከግራኝ ዋና መላከተኛ (የቃጽ ልጅ አብርሃም) በተረከበ ጊዜ «ከኛ ከእስላም ሃይማኖት ጋር የተባበረ የአዳል እስላም (ግራኝ አህመድ) አሁን የሀበሻን ምድር የሚገዛው የንጉሡን ልጅ ወደኔ ልኮታልና

(1) ስለዚህ ታሪክ ነገሥቱ እምተእጎዞቱ እስከ ርደቱ ኀበ ባሕር ፲ ዓመት ወ፯ አውራኅ ብሎ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ያደረገው ስሕተት ይመስለኛል ገጽ 120 ።

(2) ገኝ የሚባለው አውራጃ በዘመኑ ንጉሥ ያሰኛል ። አውራጃው በትክክል አይታወቅም ፤ ከፈጠጋርና ከጎድም የሚዋሰን ይመስላል ። የዘርዓ ያዕቆብ ፤ የበዕደ ማርያም ዜና መዋዕል ገጽ 14-16 47.112. 137 ።

የፈቃዱን ሳይሆን የፈቃድህን እፈጽም ዘንድ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ እዘዘኝ» ብሎ ወደ ዋናው የቱርክ ሱልጣን ወደ ሶለይማን ላከበት ። ሱልጣን ሶለይማንም «የንጉሡ ልጅ እዚያው አንተ ዘንድ ይቀመጥ ፤ በላዩም ላይ ክፉ አትሥራበት» የሚል መልእክት መልስ ስለመጣለት የዘቢድ ባሻ ከራሱ ንብረት ውስጥ ሀብት ጨምሮ ሚናስን በተለየ ሥፍራ በመልካም አስቀመጠው (1) ።

በዚህ መካከል ባለፉት ምዕራፎች እንዳነበብነው ግራኝ አህመድ በነሚናስ ለውጥና በላከው ፩፻ሺህ ወቄት ወርቅ ባገኘው የጦር መሣሪያና ወታደር ፖርቱጊዞቹን በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. በመስከረም ፫ ቀን በአሸንጌ (ወፍላ) ላይ አሸንፎ ክርስቶፎሮስን ከገደለ ወዲህ ከመጡለት የቱርክ ወታደሮች አብዛኞቹን ስለመለሳቸው እርሱ ራሱ በዚሁ ዓመት በየካቲት ወር ካፄ ገላውዴዎስ ጋር ተዋግቶ በደንቀዝ ወረዳ በዘንተራ ዓቀበት መሞቱን ባለፉት ምዕራፎች አንብበናል ።

ግራኝ ሲሞት የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አባት የግራኝን ልጅ ይዞ ታርቆ ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ መግባቱን ካስታንሆዞ ሲያመለክት የግራኝን ልጅ ስሙን አይናገርም። ታሪክ ነገሥቱ "ፈረንጆቹን ይዞ ከግራኝ ጋር ዓፄ ገላውዴዎስ ተዋግቶ ገደለው ልጁንም ማረከው ሚስቱ ግን አመለጠች" ሲል የተያዘው ልጅ ያው የባሕር ነጋሽ አባት ይዞት የገባው መሆኑን የተማረከውም የግራኝ ልጅ ስሙ ማን መሆኑን አይናገርም ።

ነገር ግን ግራኝ ከሞቷ በኋላ ባለፈው እንዳነበብነው በደዋሮ እስላሞቹ በአዳል ንጉሥ ወንድም (በወራበጎጥ ?) አዝማችነት መጥተው ከዓፄ ገላውዴዎስ ሹማምንት ተዋግተው የተሸነፉለት መሪው የግራኝ አህመድና የድል ወንበራ ልጅ ተማርከው ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ መቅረባቸውን ቢያረጋግጥም በሚናስ የተለወጠው ከደዋሮ የተማረከው አሊ ገራድ አይደለም ። ታሪክ ነገሥቱ የግራኝን አሟሟት ባወሳበት ላይ ከላይኛው ጋር በማያያዝ «የግራኝ ሚስት ማምለጥና የልጅዋ መማረክ ለምርኮኛው ለሚናስ መመለስ ምክንያት ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ» ብሎ አመልክቷል ፤ ስለዚህ በሚናስ የተለወጠው የግራኝ ልጅ የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አባት ይዞት የገባው ሌላ መሐመድ የሚባል የግራኝ አህመድና የድል ወንበራ ልጅ መሆኑን ዜና መዋዕላቸው ለይቶ ይገልጻል (2) ።

የሆነ ሆኖ የሚናስ መያዝ በእቴጌ ሰብለ ወንጌል ዘንድ የጣለውን ያህል

(1) ወሶቤሃ ፈነወ ላዕከነ ኀበ ሡልጣን ሶሌማን እንዘ ይብል ሱታፌ ሃይማኖት እስላም ዘአዳል ዘመለከ ለምድረ ሀበሽ ናሁ ፈነዎ ለወልደ ንጉሥ ኀቤየ አምኀ ለክብርከ አዚዝ (እዘዝ) ምንተ እግበር ቦቱ ይኩን ፈቃድከ ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ባሕቱ ፈቃድከ ይኩን ። ወውእቱ ተሰጥዎ ለመልእክተ ወይቤ አንብሮ ለወልደ ንጉሥ ኀቤከ በሠናይ ወኢታኅሥም ላዕሌሁ ። ወሀቦ ማኅደረ ሠናየ ወዘቱ ንብረቶ . . . . . . ገጽ 119 - 120

(2) ወበውእቱ መዋዕል አሐዘት ትትሌዓል መንግሥተ ገላውዴዎስ . . . . . ወገብረ ፀብአ ምስለ ግራኝ ወቀተሎ . . . . . . ወአኀዘ ወልዶ ፤ ብእሲቱሰ አምሰጠት ። ወተአኀዘተ ወልዱ ወአምስጦተ ብእሲቱ ኮነ በፈቃደ እግዚአብሔር ምክንያተ ለተመይጦተ ዝንቱ ወልደ ንጉሥ (ሚናስ) እም ጼዋዌ . . . . ታሪክ ነገሥት ገጽ 120 ። በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ወወሀበ ሎሙ ቤዛሆሙ መሐመደሃ ወልዶ ለኢማም አህመድ ሲል የተለወጠው እርሱ መሆኑን ይለያል ፤ ጉንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕል ገጽ 35

ጭንቅ ብድር በምድር እንደሚባለው የልጅዋ ባፄ ገላውዴዎስ እጅ ተማርኮ መቀመጥ ለድል ወንበራ ኀዘንንና ሥጋትን እሳድሯል ማለት ነው ። በዚህ ምክን ያት «አንቺም ልጄን ላኪልኝ እኔም ልጅሽን ልላክልሽ» ብላ ድል ወንበራ ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል ምጥዋ በሚገኙት የቱርክ ባለሥልጣኖች አማካይነት መላኳን ታሪክ ነገሥቱ ያረጋግጣል (1) ።

ከዚሁ አያይዞ «ልጄን ተቀብለህ ልጅዋን ላክላት» የሚል ማመልከቻ ድል ወንበራ ለሃይማኖት ወገኗ ለዘቢዱ ባሻ መላኳን የዘቢድ ባሻ የሚናስ እቀማመጥ በዋናው ሱልጣን በሶለይማን ፈቃድ መሆኑን ስለሚያውቅ የዚህን የለውጥ ነገር ለመፈጸም የድል ወንበራን የልመና ቃል ለቱርኩ ሱልጣን ማስተላለፉን ሱልጣኑም "የድል ወንበራ ልጅ የሃይማኖት ወንድማችን ስለሆነ የክርስቲያኑን ንጉሥ ልጅ ወደናቱ መልሰህ የድል ወንበራን ልጅ ከእናቱ ጋር እንዲገናኙ አድርግ» የሚል ትእዛዝ እንደመጣለት ይገልጻል (2) ።

ቢሆንም ባሻው ከሱልጣኑ ታዞ ይሁን ወይም በራሱ ፈቃድ የሚናስን ዋጋ በማስወደድ የግራኝን ልጅ መመለስ ብቻ አይበቃም በማለት ፩ሺ ወቄት ወርቅ ጨምረው ልከው ልጅዎን ይውሰዱ የሚል መልእክት ወደ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ላከ ። ንግሥቲቱም ስለልጃቸው ፍቅር ሲሉ ምንም ሳይከራከሩ ሺውን ወቄት ወርቅ ከራሳቸውም ከትግሬ ሹማምንትም አዋጥተው ከሰበሰቡ በኋላ የድል ወንበ ራን ልጅና ወርቁን ወደ ምጥዋ ላኩ ።

ISIC

በቱርኩ ባለሥልጣን ትእዛዝ የግራኝን ልጅ መሐመድን ይዘው የመጡት ክር ስቲያኖችና ሚናስን ይዘው የመጡት እስላሞች ጠብና ክርክር እንዳያነሡ ለየብቻ ቸው በመርከብ ሆነው እየተጠበቁ የልውውጡ ሥነ ሥርዓት በደንብና በሰላም ተፈጸመ ። የቱርኩ ባለሥልጣንም "በሌላው ሃይማኖት ብትለያዩም ባንዱ በእግዚ አብሔር እምነት አንድ ናችሁና ተስማምታችሁ በሰላም ኑሩ" ብሎ በመሐላ አስ ማምቶ አለያያቸው ሲል ታሪክ ነገሥቱ ያረጋግጣል ።

በዚህ ላይ የቱርኮቹ ስሜት በዚህ ዓይነት ቀዝቅዞ ወደ መልካም መንፈስ ተመ ርቶ ሁለቱን የባላጋራ ወገኖች በሰላም ተስማምታችሁ ኑሩ ብሎ ከማማግል የደረ ሰበት ምክንያት በትክክል አይገባንም ። ምናልባት የዓፄ ገላውዴዎስንና የቤርሙ ዴዝን ጠብ የንጉሡን ከካቶሊኮቹ መንግሥታት ከነ ፖርቱጋል ጋር ለመደረብ ክልብ ፈቃድ እንደሌላቸው በመመልከት ይሁን ወይም በዓረብ አገር በመልካም መስተንግዶ የኖረው ወጣቱ ሚናስ ወደ አገሩ ተመልሶ ምናልባት አንድ ቀን ወደ ዙፋኑ የወጣለት የቱርክን ሱልጣን በላይነት በፈቃዱ ሊቀበል ይችላል የሚሉ ምኞት ይኖር ይሆን ። ወጣቱ ሚናስም ከግራኝ ጋር ፫ ዓመት ፣ ከዘቢድ ፓሻ ዘንድ ፫ ዓመት በድምሩ ፮ ዓመት በኖረበት ጊዜ ዓመሉን አሳምሮ ምናልባትም ዓረብኛም እየተማረ በተቻለው ማራኪዎቹን ባለሥልጣኖች አስደስቶ ይሆናል ።

(1) ፈንቲሊት ወልድየ እፌኑ ለኪ ወልደኪ ወተሰጥወት ይእቲ በፍሥሐ ወበሐሤት ወትቤ እሆ ወተ ሰነማቀ ፪ሆን ገጽ 120

(2) ታሪክ ነገሥት ገጽ 120

ነገር ግን እንደምናነበው እነ እንድርያስ አቪዬዶ ከፖርቱጋል ንጉሥና ከሮማ
ሊቀ ጳጳስ ተልከው ለሃይማኖቱ ጉዳይ ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ ከመጡ በኋላ በዚሁ
በመጡበት ዓመት የቱርክ መንግሥት ወታደር ልኮ የምጥዋን ወደብና ደባርዋን
ሁሉ መያዙን በቀን ብዛት ታማኝና አገልጋይ የነበረውንም ባሕር ነጋሽ ይስሐቅን
አስከድቶ ወደርሱ ማስገባቱን ወደፊት በዝርዝር እናነባለን ።

በዚህ ላይ የምንመለከተው የቱርክ መንግሥት ምጥዋንና የአርኪቆን ወደ
ቦች የያዘው እንደ አው. ቍጥር ፲፰፻፶፯ ዓ. ም. ላይ ሲሆን ሚናስ በቱርክ ባለሥል
ጣኖች አማካይነት በስምምነት ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው በኢትዮጵያ አቈጣ
ጠር ፲፰፻፴፯ ዓ. ም. (እንደ አው. ቍ. ፲፰፻፵፮) ስለሆነ በዚህ ጊዜ ቱርኮች ምጥዋ
ንና አካባቢውን ገና በስፋት ባይዙም ስምምነቱን ሊፈጽም የቻለው የቱርክ ተወላ
ጅነት ያለው ያው የዘቢድ ፓሻ ይሆናል ወይም የቱርክ መንግሥት ምንም አካባቢ
ውን ገና ባይዝ በመርከብ ቀይ ባሕርን የሚቆጣጠረው አንድ የቱርክ የመርከብ ባለ
ሥልጣን ለጊዜው ወደቦቹን ምጥዋንና አርኪቆን ብቻ ይዞ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፻፵፮

### አቤቶ ሚናስ ከምጥዋ ወደ ዓይባ መጥቶ ከእናቱ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ከተገናኙ በኋላ ከዓይባ ወ[illegible] ሄዶ ከወንድሙ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር እንደተገናኘ ። (፲፰፻፵፩ ዓ. ም.)

ንግሥት ሰብለ ወንጌል ለምጥዋና ለትግሬ በሚቀርበው በዓይባ (ወገራ) ሆነው ስለ
ሚናስ ለውጥ በምጥዋ በኩል ከድል ወንበራ ጋር ሲላላኩ ዓፄ ገላውዴዎስ መቀመ
ጫቸውን ወደ ደቡብ አዛውረው አዋሽ ወንዝ አጠገብ ወጅ ከሚባለው ወረዳ ከተማ
ከትመው ተቀምጠዋል ። በዚህም ክፍል የተቀመጡበት ምክንያት ባንድ ወገን
ከትራፊው ከግራኝ ጦር ጋር ለመዋጋትና ደግሞ በዚሁ ዘመን ደዋሮን ባሌን ሊወር
የተነሣውን የጋላን ነገድ ለመከላከል እንዲመቻቸው ነው ።

ስለዚህ በዚሁ በጦርነትና በአስተዳደር ጣጣ የተነሣ ከወንድማቸው ከሚናስ
ሊገናኙ የቻሉት አቤቶ ሚናስ በተመለሰ በሦስተኛው ዓመት መሆኑን ታሪክ ነገ
ሥቱ ያረጋግጣል ። የለውጡም ስምምነት በንግሥቲቱ አማካይነት ብቻ ሊፈጸም
የቻለው በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ።

ንግሥት ሰብለ ወንጌል በዚሁ በዓይባ ሆነው የሚናስን በነፃ መለቀቅና ወደ
ርሳቸው ጉዞ መገሥገሡን እንደሰሙ ታላቅ ደስታ አድርገው ድንኳን አስተክለው
ሥጋጃ አስነጥፈው ካህናቱና ቀሳውስቱ ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰው መስቀልና
ጽና ይዘው መኳንንቱና ሹማምንቱ ሁሉ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው በታላቅ
የወታደር ሰልፍ ሲጠባበቁ ሚናስም በመላክተኞቹና በትግሬ መኳንንት ታጅቦ
መጣና እናቱ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ወንድሞቹና እኅቶቹ ወደ አሉበት እልፍኝ
አገቡት ።

በዚህ ጊዜ ስድስት ዓመታት ያህል የተለያዩት እናትና ልጅ በዚህ ሰዓት ሲገናኙ የሚሰማቸው ደስታ ልዩ መሆኑ አይጠረጠርም ። ንግሥት ሰብለ ወንጌል በዚያ በክፉው የመከራና የስደት ዘመን ፊቅጦር በሞተበት ዓመት ሚናስ ሲማረክ የተሰማቸውን ኀዘንና ለቅሶ በዚህ ቀን ደስታ ተክፍለውታል ። ይኸንኑም ራሱ ታሪክ ነገሥቱ እናቱ ባገኘችው ጊዜ አንገቱን አቅፋ እንባዋን እንደውኃ እያወረደች ሳመችው የዚህ ቀን ደስታ ተነግሮ በየገጹ ተጽፎ አያልቅም በማለት በራሱ ግዕዝኛ ቋንቋ አጋኖ ጽፎአል (1) ።

ከዚሁ አያይዞ ለዚሁ ሚናስ ለተመለሰበት ቀን ክብረ በዓል ተደርጎ ጥሩ ጥሩው መብልና መጠጥ እየተዘጋጀ ከንግሥቲቱ ዘንድ እየተላከ ባንድ አዳራሽ ካህናትና ሊቃውንት በሌላው አዳራሽ መኳንንትና ወታደር ግብር ገብተው በደስታ ይበላ ይጠጣ እንደነበረ አስፋፍቶ ተርኮታል ።

ከዚህ በኋላ ንግሥት ሰብለ ወንጌል የሚናስን ከምርኮ መመለስ የምሥራቹን የሚነግሩ መላክተኞች ወደ ልጃቸው ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ ላኩ ። ገላውዴዎስም የሚናስን መመለስ ከመላክተኞቹ እንደበት ሲሰሙ ልክ ከመቃብር እንደተነሣ ያህል ቆጥረው በጣም ተደሰቱ ። በዚህ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከዓይብ ተነሥተው ወደ ሽሜ (ዳሞት) ሄደው የክረምትን ወራት በዚያ ካሳለፉ በኋላ ሚናስ ከዓረብ አገር በተመለሰ በሦስተኛው ዓመት ከሽሜ ተነሥተው ከእናቱ ጋር ዓፄ ገላውዴዎስ ወደ አሉበት ወደ ወጅ መሄዳቸውን ንግሥቲቱ ከአቤቶ ሚናስና ከጓዛቸው ጋር ወጅ ሲደርሱ ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ገላውዴዎስ ንግሥቲቱን እንዲቀበሉ ቀደም አድርገው የላኩዋቸው የውስጥና የውጭ መኳንንት ንግሥቲቱን በክብር ተቀብለው ንጉሡ ልጃቸው ወደ አሉበት አዳራሽ ከነልጆቻቸው አግብተው እንዳገናኟቸው ዓፄ ገላውዴዎስም ከእናታቸው ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ከወንድሞቻቸው ከእኅቶቻቸው ከዓመተ ጊዮርጊስና ከነሰበነ ጊዮርጊስ ጋር ከብዙ ጊዜ በኋላ ስለተገናኙና በተለይ ደግሞ ከምርኮ የተመለሰውን ወንድማቸውን በማግኘታቸው ታላቅ ደስታ ማድረጋቸውን ታሪክ ነገሥቱ አስፋፍቶ ተርኮታል ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ግራኝ አህመድ የሞተ ጊዜ የምሥራቹን ለናታቸው ልከው እናታቸውን ከሸዋዳ ወደ ጣና ባሕር ዳር ያስመጡ ጊዜ ንግሥቲቱ ወደ ሠፈር ከመ

(1) ..... አይ ልሳን ዘይክል ነቢበ ወዚንዎ ፍሥሐሃ ለይእቲ ሰለት ወኢይትከሀል ይንገርዎ በበ ገጹ ። ወእምዝ አብእዎ ኀበ ሀለዉ እሙ ወእኁሁ ወአኀቲሁ ወሶቤሃ ሐቀፈት ክሳዶ ንግሥት ሰብለ ወንጌል ወአምኀት ዘሎ አባላቲሁ እንዘ ትበኪ ወታውኀዝ አንብዓ ከመ ማይ.... ታሪክ ነገሥት ገጽ 121 ። ጀምስ ብሩስ ፪ኛ ቮሊዩም ገጽ 216 ። የኢት. ታሪክ ጥናት ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 159 ቊ. 199 ። ወንድሙንና እህቶቹን ተሳለመ ሲል ። በዚህ ጊዜ ፊቅጦር ሞቶ ገላውዴዎስም በደቡብ ኢትዮጵያ በወጅ ስላሉ ምናልባት ከናቱና ከእኅቶቹ ጋር ሆኖ የተቀበለው ወንድሙ ያዕቆብ መሆን አለበት ። እርሱም እስከዚህ ጊዜ ድረስ በሕይወት መኖሩን ወይፈት እናንባ ሰን ።

ድረሳቸው በፊት ንጉሡ ገላውዴዎስ ከአሉበት ሠፈር ወጣ ብለው ሄደው እናታቸውን እንደተቀበሏቸው አንብበናል ። አሁን ግን እንኳን ከሠፈር ሄደው ሊቀበሉዋቸው ከአሉበት አዳራሽ እንኳን ወደ በር ወጣ ብለው እናታቸውን መቀበላቸውን ታሪከ ነገሥቱ አይገልጽም ። በዚህ ፈንታ "ወአብእዋ ውስተ ጽርሐ ንጉሥ ምስለ ደቂቃ - ከልጆቿ ጋር ወደ ንጉሡ አዳራሽ አስገቧት" ይላል ።

ለዚህ መላ ጭምር የምንሰጠው ምክንያት ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ዓፄ ልብነ ድንግል ወዲያው እንደሞቱ በ፲፰፻፵፫ ዓ. ም. የነገሡት እንደዚሁ በሕዝብና በካህናት ፈቃድ እንጂ ጳጳስ በዚያን ጊዜ ስለ አልነበረ እንደ ደንቡ በጳጳስ እጅ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው አልነገሡም ። በጳጳስ ተቀብተው ባልነገሡበት ዘመን እናታቸውን ከሩቅ ሄደው ተቀብለው ወደ ሠፈር አጅቦ ለማምጣት ዘመናዊው ሥነ ሥርዓት አይከለክልም ኖሯል ማለት ነው ።

አሁን ግን ባለፈው እንዳነበብነው ጳጳሱን አቡነ ዮሳብን ከእስክንድርያ ካስመጡ ዘንድ ምንም እንኳን ታሪከ ነገሥቱ ባያወሳው በጳጳሱ እጅ እንደ ደንቡ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው ሥርዓተ ንግሣቸውን ማደሳቸው ስለማይቀር የተቀባ ንጉሥ ደግሞ እናትንም ቢሆን ልጅን አባትንም ቢሆን ወንድምን በዙፋኑ ተቀምጦ ይቀበላል ፤ እጅ ያስነሣል እንጂ ከዙፋኑ እንደማንም ሰው ተነሥቶ ከደጅ ወጥቶ በሰው መካከል እናቱንና ወንድሙን ስሞ አይቀበልም የሚሉ ንጉሣዊው ሥነ ሥርዓት ይከለክል ይሆናል። በዚህ ምክንያት ዓፄ ገላውዴዎስ ፫ ዓመት ያላዩዋቸውን እናታቸውን ሰባት ዓመት የተለያቸውን ወንድማቸውን እነዚያ አገር አቋርጠው ከዳሞት ሲመጡ እርሳቸው ከአዳራሻቸው ወጥተው አልተቀበሉም ማለት ነው ። ከውስጥ ከገቡ በኋላ ግን የሆነውን የአቀባበል ዓይነት ከዙፋናቸው ተነሥተው እናታቸውንና ወንድማቸውን አቅፈው ስመው ይቀበሉ ወይም እንደተቀመጡ እጅ አስነሥተዋቸው በኋላ ወደ ሌላ ክፍል ተዛውረው የናትና የልጅነቱ እንደዚሁም የወንድማማችነቱ ግንኙነት በመሳሳም ይፈጸም አናውቅም ።

## ምዕራፍ ፻፵፮

## የቱርኮች እንደገና ከምጥዋ ወጥተው ደብረ ዳሞን ማፍረስና ኤርትራን መውረር - የባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ከዳቱና ሞቱ ።

ስለቱርክ አነሣሥና በምን አኳኋን ቀዳማዊ ሰሊም መካከለኛውን ምሥራቅ ፤ ግብጽን እየወረረ እንዳስገበረ በምዕራፍ ፲፰ ላይ ልጁ ዳግማዊ ሶሊማን በምን አኳኋን የግሪክን የባልካንን አገሮች ሁሉ እስከ ቪዬና ድረስ አስገብሮ እንደገዛ በሰሜን አፍሪካ ግዛቱን ከቀድሞው የበለጠ እንዳስፋፋ በየግዛቱ ከርሱ የሚሾሙት በጽናት ዋናውን የሱልጣኑን መንግሥት ኃያል እንዳደረጉት በግብጽ የሚሾመው ፓሻ እየተባለ በፓሻሊክ ማዕርግ ግብጽንና አካባቢውን በሱልጣኑ ስም እንደሚያስተዳድር ከነዚሁ አንዱ ሶሊማን ፓሻ ከሱዌዝ የጦር መርከቡን ይዞ ወደ ሕንድ አገር ዘምቶ

የፖርቱጋሎችን የወደብ ከተማ ዲውን ሊመታ በዘመተበት ጊዜ ሲሄድና ሲመለስ እግረ መንገዱን የዓረብን አውራጃዎች መስታንን ሐድራሞትን አደንን የመንን በምን አኳኋን እየወጋ እንዳስገበረ በ፲፭ እና በ፲፮ ምዕራፎች አንብበናል ። የቀሩ ትም የዋናው ሱልጣን እንደራሴዎች በአውሮፓም በኩል በምሥራቅም በፋርስና በሰሜን በመስኮብ ግንባር በጦርነት እየተዋጉ ግዛት ማስፋት ካገር ላይ ተወላጁን ወጣት ለወታደርነት እየመለመሉ ወታደሩን ማደርጀት በደረጀው ወታደር አዲስ ግዛት መጨመር በኃይል ይዘው ከሚገዙት አገር ላይ በግብርና በገጸ በረከት ብዙ ሀብት እየሰበሰቡ ወደስጣንቡል እየላኩ የዋናውን የሱልጣኑን መንግሥት አከበሩት ።

በዚህ ዓይነት መቀመጫው ስጣንቡል የሆነው የሱልጣን ቤተ መንግሥት እንደ ጽርሐ አርያም የራቀ ደጁ ደርሶ ለመሳለም ሱልጣኑን ለማየት እንደ አንድ ብርቅ ነገር የሚቆጠር ሆነ ። በተለይ ዘሩ ነገዱ ቢለያይም ሃይማኖቱ እስላም ለሆነው ሁሉ የቱርክ ሱልጣን መመኪያና ተስፋ ሆነ ።

በነርሱ አጠራር ባብ. ኢ. ኡማዩን የሚባለው ፈረንሳዮች "Sublime Port" ከፍተኛ በር የሚሉት እ. አ. ቆ. በ፲፮፻፶፬ ዓ. ም. በነጭና በጥቁር ዕብነ በረድ አጊጦ የተሠራውና ሳራይ ወደሚባለው ወደ ሱልጣኑ ቤተ መንግሥት የሚያስገባው አስደናቂ ነው ። በርሱም ግራና ቀኝ አንድ አንድ ጊዜ በጥፋት የተገኙ አንገታቸው በቅጣት የተቆረጠ ጭንቅላት ይሰቀልበታል ።

በዚህ ባፄ ልብነ ድንግል ባፄ ገላውዴዎስ§ፙፄ ሚናስ ዘመነ መንግሥት በስጣንቡል ታላቅ ዙፋን የተቀመጠው ከዚህ በፊት ከሻርል ፷ኛ ጋር የተዋጋው ሶሊማን የሚባለው ነው ። እርሱም በአውሮፖች ዘንድ "Magnifique" አስጉምጅ" በቱርኮች ዘንድ "ካኑኒ - ሕግ አጋጊው" የሚሉ ስያሜ ወጥቶለታል ። የርሱም ገዥነት ከ፲፭፻፳ እስከ ፲፭፻፷፮ ዓ. ም. ድረስ ተራዝሞ ፵፮ ዓመታት ገዝቷል ። ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ሥልጣኑ በመሬትና በባሕር ላይ ስለተስፋፋ የብዙ መንግሥታት አገሮች ጌታ ፤ እንደዚሁም በብዙ ሱልጣኖች ላይ በበላይ ሆኖ ስለሚያስተዳድር ከመጠሪያ ስሙ የሚቀጥለው የማዕርጉ ሥያሜ ፤

የሱልጣኖች ሱልጣን

የዘውዶች አዳይ (ዘውድ ሰጥቶ ንጉሥነትን የሚፈቅድ)

የባሕሮችና የአህጉሮች ጌታ ይባላል ።

በቅርቡ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚመለከተው ባለፈው ሁሉ እንደተጻፈው ከቀይ ባሕር ማዶ በዓረብ አገር ያለው የዘቢድ ፓሻ ብቻ ሳይሆን አንድ አንድ ጊዜ ከርሱ የበላይ ሆኖ የሚታየው በካይሮ የሚሾመው ፓሻ ነው ። ከርሱ ሥር ፯ ወይም ፰ የሚሆኑ አግኪ የሚባሉ በተለይ የሚሾሙ የጦር መኰንኖች ፤ ኤሚር ኤል ሐጂና ሙፍቲ ፤ አላማ የሚባሉ ተግባራቸውና ማዕርጋቸው የተለያየ የሃይማኖት መሪዎች አሉ ።

ሶሊማን ፓሻ እንደ አው. ቆ. ፲፭፻፴፰ - ፴፱ ዓ. ም. ወደ ሕንድ ዘምቶ ከተመለሰና ወደ ስጣንቡል ሄዶ በግዞት ከተቀመጠ ወዲህ በግብጽ ግዛት ፤

ዳውድ ፓሻ ......................... ከ፲፰፻፴፱ - ፲፰፻፵፱ ዓ. ም.
አሊ ፓሻ ...................... ከ፲፰፻፵፱ - ፲፰፻፶፬ ዓ. ም.
መሐመድ ፓሻ ........................ ከ፲፰፻፶፬ - ፲፰፻፶፰ ዓ. ም.

ድረስ እየተከታተሉ ከገዙ ወዲህ ከነርሱ ቀጥሎ ፓሻ እስከንድር ፤ ፓሻ አሊ ፓሻ ኤል ሳፊ የሚባሉ በደካማነት ለጥቃቅን ጊዜ አስተዳድረዋል ።

የሆነ ሆኖ ባሁኑ ባዬ ገላውዴዎስ ጊዜ ግራኝ አህመድ ከሞተ በኋላ ንጉሠ ነገ ሥቱ በደቡብ ክፍል ባሉበት ሰዓት ሚናስም በአሊ ገራድ ተለውጦ ወዳገሩ ከተመ ለሰ ወዲህ ከ፲፰፻፵፱ ዓ. ም. ጀምሮ የቱርኮች የመርከብ ኃይል እየቀረቀሰ ምጥዋን ይዞ ከቆየ በኋላ በ፲፰፻፶፰ ዓ. ም. እስከ ደባርዋ ደርሶ ሰሜን ኢትዮጵያን የወረረው የቱርክ ጦር በአሊ ፓሻና በመሐመድ ፓሻ ዘመን መሆኑ ነው (1) ።

ስለዚህ ዓዬ ገላውዴዎስ ግራኝ አህመድን በማሸነፍ የመዠመሪያ ጊዜ ደስታ ቸውን ከእናታቸውና ከፖርቱጋሎቹ ጋር ከአሳለፉ በኋላ ቀጥሎም ከግራኝ በኋላ በደቡብ ክፍል በባሌ በደዋሮ በፈጠጋር የነገሠውን ወዚር አባስንም ቢገድሉ የግራኝም የርሱም ሞት ተከታትሎ ቢደርስ በብዙ ወገን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ተቀ ጣጥሎ ባንድ ዘመን ላይ ብዙ ችግር እንደተፈጠረባቸው ባለፈው አመልክተናል ።

የሃይማኖቱ ጉዳይ ባለፈው እንዳነበብነው ከብዙ ክርክር በኋላ ውሳኔ ቢደረ ግለትም ቀድሞ እነቤርሙዴዝ የነበሩ ጊዜ በደዋሮ በኩል የተነሣው የጋላ ወረራ ባሁኑ ጊዜ እየባሰበት ሄዲል ISIC ዶዚያ ራሳቸውም እየሄዱ ጦርም እየላኩ በሚያዋ ጉበት ሰዓት በሰሜን በኩል ደግሞ የቱርክ መንግሥት ምጥዋን ከያዘ በኋላ ከዚያ አልፎ ደባርዋን ወረረ ፤ ለመውጣት አስቸጋሪ የነበረውን የደብረ ዳሞን ገዳም ዘረፈ ። ገዳሙን አፈራርሶ መነኲሳቱን ፈጃቸው የሚሉ ወሬ መጣላቸው ።

በዚህ ዓይነት በብዙ ጉዳይና ጦርነት መቸገራቸውን በማውሳት ታሪከ ነገሥቱ "እምለፌ ይትዋሰዖሙ ለአፍርንጅ" ባንድ ወገን ከፈረንጆቹ ይከራከራል ካለ በኋላ "ወእምካልእትሂ ለፌ ኮነ ሀልወ እንዘ ይመክር በዘይፀብዖሙ ለወንድ ዘለወ ንድ ዘውእቱ ትርክ ወያስተዳሉ ፃእፅዓ ቀትል ወያስተሐምም በእንተ ዓቂበ አህጉ ራት እምፀብእ ጋላ" ያለውን ከዚህ በፊት አንብበናል ።

በአሁኑ ጊዜ ስለሆነው ስለቱርኮች አመጣጥ ስለ ውጊያቸውም ዝርዝር የሚነ ግረን አጻጻፉ ባጭሩ ቢሆንም ለኢትዮጵያ ታሪክ መሠረትም ምሰሶም የሆነው ታሪከ ነገሥት ነው ። እርሱም ዓዬ ገላውዴዎስ በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት ገዳማትና ወረዳዎቹ በባሻ ዑዝድሚር (2) ሠራዊት መያዛቸውን ንጉሡ ሰምተው አዝነው ሳለ የበለጠ ደግሞ ቱርኮች ደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ወጥተው በዚያ የሚገኙትን ጻድ ቃንና ደጋግ ሰዎች መግደላቸውን በተለይም ጻድቁ ንጉሥ ልብነ ድንግልና የደን

(1) Chronologie de la Nafion Egyptienne-Joseph Gataui Pacha. ገጽ 304 - 314
(2) አንዳንድ ጊዜ ውዝሚዶር የሚናስ ዜና መዋዕል እስድሙር ሌላው ጽሑፍ ደግሞ ዝሙር ይለ ዋል ።

ቹና የጻድቃን አባት የሆኑትን አባ አረጋዊ የተቀበሩበትን ገዳም ገብተው ማርከሳ ቸውን በሰሙ ጊዜ ሰውነታቸው በኀዘን መውደቁን ያረጋግጣል (1) ።

በዚህ ጊዜ ደግሞ በጣም የሚያሳዝነው ባለቀትም ምዕራፎች እንዳነበብነው ፖርቱጋሎች በመጡበት ሰዓት በመቀበልና በማስተናገድ ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋር በማገናኘት ለመጣው መድፍ መጉተቻ ከብት በማቅረብ ስንቅ በመስጠት አብሮ በመዋጋት ያን ያህል ያገለገለው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በአሁኑ ጊዜ ለቱርኮች ገብቶ ዋና የመግቢያና የወረራ መሣሪያ መሆኑ ነው ። ታሪክ ነገሥቱ የከዳበትን ምክንያት አልጻፈውም ። ምናልባት ላለፈው አገልግሎቱ የሚመጥን ሹመትና ግዛት ወይም ሽልማትና ማዕርግ አልተሰጠኝም ብሎ ተቀይሞ ይሆናል ። የርሱ ከዳተኝነትና ድጋፍ ባይጨመር ኖሮ ቱርኮች ከምጥዋ ለመውጣትና እስከ ደባርዋ ደርሰው ኤርትራን ለመውረር ባልቻሉ ነበር ።

ከዚህ እያይዞ ታሪክ ነገሥቱ ፓሻ ዑዝድሚር ሠራዊቱን በየአለበት በትግሬ ወረዳ ልኮ አገር ሲያዘርፍ ከብትና ሰው ሲያስማርክ በቡር አገር ወታደሮቹ ያር ሰው ሳለ ፈላሒን (ገበሬዎች?) የሚባሉ የአገሩ ሰዎች ተዋግተው ብዙዎቹን እንደ ገደሏቸው በዚሁ ጊዜ ወደ ነርሱ ገብቶ የሚያገለግለውን በተቀባው ንጉሥ ላይ መላ ሰን ይመዝ የነበረውን ይስሐቅን ገድለው ጭንቅላቱን ቆርጠው ላፄ ገላውዴዎስ እንደላኩላቸው ያረጋግጣል (2) ።

ከዚያም የቱርኩ ፓሻ ዑዝድሚር በደባርዋ ISIC ተማ ትልልቅ ቅጽርና ቤቶች ሠርቶ በዚያም ከእስጣንቡል ፤ ከግብፅ ፤ ከዘቢድ ፤ ከጀበል ፤ ከዓረብ አገር ሁሉ ከሀበሻ አገሮችም የተሰበሰበ ወርቅና ብር ዕንቍ ልዩ ልዩ ልብስና ሀብቱን የሰለዋን ንግሥት ጋልዋን በዚያ እንዳለች ከትንሽ ወታደር ጋር ትቶ እርሱ ራሱ በ፰፻ ፈረሰኛ በብዙ ጠበንጃና ጦር በያዙ ሰይፍ በታጠቁ በብዙ የእግረኛ ወታደሮች ታጅቦ ከደባርዋ የትግሬን ግዛት ሁሉ አቋርጦ ወደ መዘጋ ሲሔድ ከበረሃው አገር ሲገባ የንዳድ በሽታ አሞት ወደቀ ። በጣም በትኩሳት ከመታመሙ የተነሣ ጭፍሮቹ በቃሬዛ ይዘውት ይጓዙ ገጠመር ።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ተደካክመው ሲጓዙ ንግሥት ጋስዋ (የመዘጋ ንግሥት) የዓፄ ገላውዴዎስ የጦር አለቃ በየጊዜው ከርሷ ጋር እየተዋጋ ወንድሟንም ገድሎ ብዙ አገር ይዞባት ነበርና ለዚህ ሁሉ ፓሻው እንዲረዳት ብዙ ገጸ በረከትና ስጦታ ይዛለት መጣች ።

(1) ወአመ ፲ወ፪ ዓመት እመንግሥቱ እንዘ ሀሎ ትእዛዘ በእንተ ሙስና እድራባት ወአዕፃዳት በእደ ዊሆሙ ለሠራዊተ ዑዝድሚር ዘውእቶሙ ትርክ ወእንዘ ውእቱ ጽምሕዋይ ፈድፋደ በእንተ ዓረ ንቶሙ ለትርክ መልዕልተ ደብረ ዳሞ . . . . . ወበዊያቶሙ ውስተ መካነ ቅዱስ ዘተቀደሰ በንብረተ ዓፅም ቅዱስ . . . . . . ዘንጉሥ ጻድቅ ልብነ ድንግል ወተቀብሮቶሙ ሕየ ለአለ አባ አረጋዊ ዘመደ ኄራን ወጻድቃን . . . . . ጕንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕል ገጽ 74 ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 110 ።

(2) ጕንዘልማን . . . . . . . . ገጽ 75 - 76 ።

ፓሻው ከንግሥቲቱ ጋር በመዘጋ በመቆየቱ በደባርዋ ትቷቸው የሄደው ቱር ኮች በረሃብና በጥም በቅጽራቸው ውስጥ እንዳሉ ተቸገሩ ። ያከማቹት እህል የቆፈ ሩት የጉድጓድ ውኃ አለቀ ። ከቅጽራቸው (ምሽጋቸው) ወጥተው እህልና ውኃ እን ዳይፈልጉ አገሬው በቀስት እየመታ ይወጋቸው ዠመር ።

በዚህ ምክንያት ያላቸውን የራሳቸውንና የሰላዋን ንግሥት ሀብት ጭነው በሌ ሊት ከደባርዋ ምሽጋቸው ወጥተው ወደ ባሕር ወደብ (ምጥዋ) ለመሄድ ሲጓዙ እነ ዚያው ፈላሒን የሚባሉት ያገሩ ሰዎች በሰይፍ ተዋግተው ፈጅተው ሀብታቸውን ሁሉ ማረኩት የሰላዋም ንግሥት ከነሀብቷ ተማረከች ። ምርኮውም ሁሉ ከቱርክ ሱልጣን ከሶለይማን ሥዕልና ሰንደቅ ዓላማ ጋር በዚሁ ዓመት በኅዳር ወር ለዓፄ ገላውዴዎስ ቀርቦላቸው በዚሁ ንጉሠ ነገሥቱ ተደስተው ምሥጋና ለእግዚአብ ሔር ማቅረባቸውን ታሪከ ነገሥቱ ያረጋግጣል (1) ።

መቼም የአገሩ ጌታ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ አገሩንና ንጉሡን ከድቶ ለፓሻው ከገባለት ለመዠመሪያው ጊዜ ትግሬን ለመውረር አዳጋች አይሆንበትም ። እነዚ ያው ከግራኝ አህመድና ከወዚር አባስ ጋር ሲዋጉ የኖሩት የትግሬ ሰዎች ወይም ልጆቻቸው በዚህም ጊዜ የመጣውን ቱርክ ፤ አገሩንና ንጉሡን የከዳውን ባሕር ነጋሽ ይስሐቅን መከተው ስለ አገራቸውና ስለ ንጉሣቸው ተዋግተዋል ማለት ነው ። ግዕዙ ሰብአ ሀገር ፈላሒን የሚላቸው የአገሩ ሰዎች ውጊያውንም በደባርዋ ዙሪያ ስላደረገው ደባርዋንም ከበው የነበሩት ከመንገድም ቱርኮቹ በሌሊት ወደ ምጥዋ ሲጓዙ ተዋግተው ሀብታቸውንና የሰላዋን ንግሥት የማረኩት እነሱው ስለ ሆኑ እነዚህ ሰዎች የዚያው የዠግናው የተሰፋ ልዑል ዓቃጽን ሠራዊ ወገኖች መሆ ናቸው ነው ። የደብረ ዳሞ ተራራ በዚያ ሁሉ የመከራ ዘመን ለግራኝ እንኳን እቅቶ ሳይደፈር ኖሮ አሁን የተደፈረበት ዋናው ምክንያት የገዥው የባሕር ነጋሽ ይስ ሐቅ ከዳተኝነት መሆን አለበት ። ከከዳቱ በፊት የሚያውቁት መነኰሳት ለንጉሡ ታማኝነቱን የቀጠለ መስሏቸው ገመድ ከላይ ልከውለት ከወጣ በኋላ እርሱ ደግሞ ለቱርኮቹ ገመድ ወይም ጠፍር ልኮ አስወጥቷቸዋል ማለት ነው ።

በተረፈ ግራኝ ዓፄ ልብነ ድንግልን በትግሬ በጸለምትና በወገራ እያባረረ ለመ ያዝ ያለዕረፍት በሚያሳድድበት ዓመት በ፲፭፻፴፯ ዓ. ም. በየካቲት ወር የመዘጋ ባላባት መከተርና ግራኝ በምን አኳኋን ተገናኝተው እንደተዛመዱ እናስታውሳለን ። አሁንም ከግራኝ ሞት በኋላ ዓፄ ገላውዴዎስ በየአለበት አገር ሲያቀኑ በመካከሉ እንደገና የቱርክ የጦር ኃይል መጥቶ ደባርዋ ከተማ ስለተቀመጠ ላዔ ገላውዴዎስ ጦር መገበር ያልፈለገችው የሰላዋ ንግሥት ሀብቷን ይዛ በመሪ ደባርዋ ገብታለች ማለት ነው ። ባሁኑ ጊዜ የመዘጋዋ ንግሥትም ምናልባት የመከተር ልጅ ትሆና ለች ። እርሷም ሽፍታ የዓፄ ገላውዴዎስ ጦር ስለከበባት ወደርሱ ለመምጣት አለመ ቻሏን ከሰላዋ ንግሥት ሰምቶ ወደ መዘጋ ሲሄድ የእርግጭሆና የመተማ በረሃ አውኮት ወባ ታሞ ሳለ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደሚባለው የመዘ

(1) ታሪከ ነገሥት ገጽ 110 - 111 ። ጉንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕል ምዕ. 85 - 87

ISIC

ጋን ግዛት ለመጨመር ሲጣጣር ከወዲህ ደባርዋ ትቷቸው የሄዱት ወገኖቹ በረኅ ብና በጥም አልቀዋል ባያልቁም በፈላሒን ሕዝብ ተሸንፈዋል ማለት ነው ። የመዘ ጋዋ ንግሥት ሃይማኖቷ እስላም በመሆኑ መከትር (ሙክታር) ከግራኝ እንደተደረበ አሁንም እርሷ ከቱርኮቹ ብትደረብ አያስደንቅም ። ስለዋ ግን የሚገኘው በወዲህ በትግሬና በላስታ መካከል ሆኖ ንግሥቲቱ እስላም መሆኗና መደረቧ ያጠራጥራል ።

የሆነ ሆኖ የቱርክ መንግሥት በዚህ ዓይነት ለጊዜው የመስፋፋት አሳቡ ይሰናከል እንጂ ከምጥዋና ከአካባቢው ፈጽሞ ሊርቅ አልቻለም ። እንደዚሁ ካፄ ገላውዴዎስ በኋላ ወንድማቸው ሚናስ በነገሡበት ጊዜ ይልቁንም በሚናስ ልጅ ባዔ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት እንዳሁኑ እምነው የሾሙት ሌላው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ሌላ የቱርክ ፓሻ ኤርትራን በወረረ ጊዜ ከድቶ መሣሪያ ስለሆነ ለንጉሡ የታመነው ዕቁበ ሚካኤል የቱርኩንም ፓሻ ባሕር ነጋሹንም ተዋግቶ አሸንፎ የሁለቱንም ጭንቅላት ቆርጦ ግዳይ ጥሎላቸዋል (1) ።

## ምዕራፍ ፶፬
## ያፄ ገላውዴዎስ ከያዕቆብና ከሚናስ ጋር መስማማት ፤

ከዚህ ዓፄ ልብነ ድንግል አራት ወንድ አራት ሴቶ[illegible]ጆች ትተው መሞታቸውን በፊት ሳናወሳ አልቀረንም ። ከአራቱ ወንዶች የመዠመሪያው ልጅ ፊቅጦር በጦርነት ብቻ ሲሞት እነሆ ሦስቱ ገላውዴዎስ ፤ ያዕቆብ ፤ ሚናስ በአሁኑ ሰዓት በሕይወት መኖራቸውን ታሪክ ነገሥቱ ያወሳል ። ከነዚህ ከሦስቱ ደግሞ በፍጹም ስሙ በደጉም በክፉም ሳይነሣ የኖረ ያዕቆብ ነው ።

ያዕቆብ እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አጻጻፍ የሁሉም ታናሽ ቢሆንም እንደ ሟቹ ወንድሙ እንደ ፊቅጦር ባይዋጋም ወይም የተዋጋው ሳይጻፍለት ቢቀር እንደ ቀሩት ወንድሞቹ እንደ ገላውዴዎስና እንደሚናስ የመንገሥ ዕድል ሳይገጥመው ቢቀርም ፤ ወደፊት ባለው ጊዜ በጐንደርም በሸዋም መንግሥቱን የመሩት ነገሥታት የርሱ ተወላጆች መሆናቸው በየመጽሐፉ ተገልጿል ። እርሱም ገራም ፋሲልንና ሥግወ ቃልን ስለወለደ ፋሲል ሱስንዮስን ወልዶ እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ መነሣት ድረስ በኃይልም በድካምም በጐንደር የነገሡት የርሱ ዘሮች ናቸው ፤

በወዲህ ደግሞ በሸዋ ያዕቆብ ሥግወ ቃልን ሥግወ ቃል ወረደ ቃልን ፤ ወረደ ቃል ሰንበልትን ፤ ሰንበልት ነጋሢን ይወልዳል ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ግን ወረደ ቃልን ሰንበልትን ሳይጨምሩ ሥግወ ቃል ነጋሢን ፤ ነጋሢ ስብስቴን ፤ ስብስቴ አብዬን ፤ አብዬ አምኃ ኢየሱስን ፤ አምኃ ኢየሱስ አስፋ ወሰንን ፤ አስፋ ወሰን

(1) የኢት. ታሪክ ካፄ ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ ከገጽ 78 - 82

ወሰን ሰገድን ፤ ወሰን ሰገድ ሣህለ ሥላሴን ይወልዳል ብለዋል (1) ።

አሁን በዚህ ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡበት ዘመን የሚናስና የያዕቆብ መገኘት በመንግሥቱ አቅዋም ላይ ትንሽ ሥጋት ሳያመጣ የቀረ አይመስልም ። ከዚህ በፊት አንዱ የነጋሢ ልጅ ባባቱ ኑዛዜ በባለሥልጣኖች ፈቃድ ከነገሠ በኋላ የቀሩት ወንድሞቹና የነጋሢ ልጆች ያለፈቃዳቸው እየተያዙ በየአምባው በግዞት መቀመጣቸውን በዚህ ዘመን የነገሥታት ልጆች ዋና የማጋዣው ቦታ ያ ግራኝ በመጨረሻ በብዙ ችግር ደርሶ ያፈራረሰውና ሀብቱን የበዘበዘው የአምባ ግሼን ወይም የአምባ ነገሥት ተራራ መሆኑ ብዙ ጊዜ ተመልክቷል ።

ነጋሢ ወይም የነጋሢ ልጅ ለግዞት ወደ አምባ ነገሥት የሚላክበት የነጋሢው ዕድሜ ከስምንት ዓመት በላይ ኖሯል ። ይኸንንም የሚያስረዳን ከናዖድ ልጆች አንዱ ከዕለታት አንድ ቀን ንጉሡ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ ገብቶ ያልሆነ ቃል ቢናገር አንድ መኰንን "ይኸ ልጅ እኮ ስምንት ዓመት አለፈው" ቢል ልጁ ደንግጦ "አዎን ለአምባ ግሼን ደርሻለሁ" ብሎ በለቅሶ መለሰ ። በዚያን ጊዜ ዓፄ ናዖድ በልጃቸው ልቅሶ ልባቸው በኀዘን ተነክቶ "ከልጆቼ ማንንም ወደ አምባ ግሼን አልሰድም" ብለው በመኳንንቱ ፊት ማሉ መባሉን ፤ ያለቀሱትም ዓፄ ልብነ ድንግል ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ከዚህ በፊት አውስተናል ።

በዚህ አጻጻፍ ይኸን የግዞት ሕግ ለመዠመሪያ ጊዜ የሰረዙ ያፄ ልብነ ድንግል አባት ዓፄ ናዖድ መሆናቸውን ከመረዳት ጋር ምንም በተራራው ላይ ምግቡም ትምህርቱም ለመሣፍንት አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ ባይጐድል ይህ የአምባ ግሼን የግዞት ኑሮ የነገሥታቱን ልጆች ምን ያህል እንዳስመረረ እንረዳለን ። በዚሁ መሠረት ዓፄ ልብነ ድንግልም አራቱን ወንዶች ልጆቻቸውን ወደዚህ ተራራ መላካቸውን የሚናገር ጽሑፍ ስለሌለ የአባታቸውን የውሳኔ አርአያ ተከትለዋል ማለት ነው ። ነገር ግን ይህ ውሳኔ ከዚያ ወዲህ በጐንደር መንግሥት በየጊዜው ልንገሥ ባይ ወሬኛ ብዙ ጊዜ እየሸፈተ አገር እያስሸፈተ ስላስቸገረ ሕጉ ሲፈርስም ሲጸናም ኖሯል ።

ስለዚህ አሁን ከእናታቸውና ከነሚናስ ንጉሡ በፍቅር ተገናኝተው እንደሰነበቱ ውለው አድረው ባለሥልጣኖቹና መኳንንቱ ይኸን የመጋዝና በነፃነት የመቀመጥ ሁኔታ አመዛዝነው በንጉሡ ባፄ ገላውዴዎስና በወንዶሞቻቸው መካከል አንድ በግልጽ የታወቀ ስምምነት ማድረጋቸውን ታሪክ ነገሥቱ ከነሚናስ ጋር በፍቅር ተገናኙ ካለው ቀጥሎ ከዚህ እንደሚከተለው ያመለክታል ።

፩ኛ. ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ አባቶቻቸው ወንድሞቻቸውን በእሥራትና በግዞት ያስቀምጧቸው እንደነበረ ለመንግሥታቸው ቀንተው በወንድሞቻቸው በሚናስና በያዕቆብ ላይ ክፉ እንዳያስቡ ።

ያዕቆብና ሚናስም ኢሳው በወንድሙ በያዕቆብ ላይ እንዳሰበው ያለ ክፋት (2)

(1) ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 34

(2) ዘፍጥረት 33 - 37

ሳያስቡ የወንድማቸው የገላውዴዎስ ዕድሜያቸው እንዲረዝም መንግሥታቸው እንዲጸና እንዲመኙ ። የዚህም እቅጩ ትርጓሜ ዙፋን እኛም ይገባናል ብላችሁ በር ሳቸው ላይ አትሸፍቱ እርሳቸውም በዚህ ጠርጥረው አምባ ግሼን ልከው እያግዚ ችሁ ነው (1) ።

ታሪክ ነገሥቱን የጻፈው ካህን ፫ቱ ወንድማማቾች ይኸን በመሰለ ተግባር (ስምምነት) ብዙ ዘመን ማድረጋቸውን ከአመለከተ በኋላ የራሱን ሐተታ በመጨመር ስለዚች መንፈሳዊ ስምምነት ከዚህ በፊት ወንድማማቾች ባንድነት ሲያስቡ እንዴት መልካም ነው እንዴትስ ያምራል ብሎ ዳዊት የተናገረውን ጠቅሶ ጉዳዩን ይዘጋል (2) ።

በዚህ ዓይነት ስምምነት ከቆዩ በኋላ ያዕቆብ አባስ በሞተ በአራተኛው ዓመት መሞቱን ታሪከ ነገሥቱ ስለሚገልጽና አባስ የሞተው በ፲፰፻፴፯ ዓ. ም. ስለሆነ ያዕቆብ የሞተው በ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ነው ማለት ነው (3) ። ሚናስ ግን ገላውዴዎስ ከኑር ጋር ተዋግተው በ፲፰፻፶፩ ዓ. ም. ሲሞቱ ከገላውዴዎስ ቀጥሎ መንገሡ ወደ ፊት ይገኛል ።

## ምዕራፍ ፻፵፱
## የጋሎች አመጣጥና የዘSICዳቸው

ስለ ጋሎች አመጣጥና ሥሪት በመጽሐፍ መልክ ለመዠመሪያ ጊዜ በግዕዝ ቋንቋ የጻፉ አባ ባሕርይ የሚባሉ የብርብር (ገሙ ጐፋ) መነኩሴ ናቸው ። እርሳቸውም የነበሩበት ጊዜ በልብነ ድንግልና በዚያው በወረራው በገላውዴዎስ ዘመን ስለሆነ ሁኔታውን በቀጥታ ያዩና የሰሙ ስለሆነ ለጽሑፋቸው ዋጋ መስጠት ይገባል ። በመ ጽሐፋቸው በ፪ኛው ክፍል ላይ የገሞን አገር ዳዊ ያጠፋው ጊዜ እርሳቸውም ገንዘባ ቸው ተማርኮ ከአገራቸው እንደተሰደዱ ያረጋግጣሉ (4) ። ከዚያ ወዲህ ግን እኝህ

(1) ወእምድኅረ ጉንዱይ መዋዕል ኮነ ተሰናዕዎ ማዕከለ ዝንቱ ንጉሥ ወአኃዊሁ ሠናያን ምግባር፡ ያዕቆብ ወሚናስ እስመ ሰሰለ ትሕዝብት እምኔሁ ከመ ኢየሐሲ እኩየ ላዕሌሆሙ በእንተ ቅንዓተ መንግሥት ወኢይግበር ቦሙ በከመ ገብሩ አበዊሁ በአኃዊሆሙ ዘከመ ሙቃሔ ወግዕዘት ። ውእቶሙኒ ኢይሔልዩ ወኢይፍቅዱ ላዕሌሁ እኩየ ከመ ሐልዮተ ኤሳው ላዕለ ያዕቆብ እኁሁ እለ ይትሜነዩ ርትዓተ መንግሥቱ ወኑኃ ሕይወቱ ወበዘከመዝ ግብር ነበሩ ጕንዱየ መዋዕለ ።

(2) ኦ ለዛቲ፡ ተሰናዕዎ መንፈሳዊት ዘተብህለ በእንቲአሃ "ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሔልዉ አኃው ኅቡረ" መዝ. ዳዊት ፻፴፪ ። ታሪከ ነገሥት ገጽ 121 - 122 ።

(3) Liber Axum. C. Rossini ገጽ 70

(4) ወለዝንቱ ነቢይ (ራሳቸው አባ ባሕርይ) ሰደዶ ዳዊ (ጃዊ) ወአጥፍአ ሀገር ዘገሞ ወማኅረከ ኵሎ ዘአጥረየ . . . ." ዜናሁ ለጋላ ጉዳዲ ያሳተመው ኮንቲ ሮሲኒ ባሳተመው የሠርፀ ድንግል ዜና መዋዕል ውስጥ ክፍል ፪ ገጽ 224

ሰውዬ በሕይወት ኖረው የዓፄ ሠርፀ ድንግል "ቁስ ሐፄ - ንስሐ አባት" እስከ መሆን ደርሰዋል ።

ፈረንጆቹ ለስነ ጽሑፍ ዋጋ በመስጠትና በማራባት ከኛ የበለጠ የአእምሮ ዕውቀታቸውም የገንዘብ አቅዋማቸውም ስለሚበልጥ የአባ ባሕርይ መጽሐፍ የእጅ ጽሑፍ ወደ ውጭ አገር ሄዶ በሎንዶንና በቪዬና ስለተቀመጠ ከዚያ ላይ ኢኖ ሊትማን ወደ ጀርመንኛ፣ኢኛሲዩጉዪዲ ወደኢጣልያንኛእየተረጐሙ በማተሚያ ካራቡት በኋላ ይኸው መጽሐፍ ኮንቲ ሮሲኒ ከተረጐመው ከሠርፀ ድንግል ዜና መዋዕል ጋር ደርቦ ወደ ፈረንሳዊ ተተርጉሞ ( louvain ) (ቤልዥክ) የሚቀመጠው ( Corpusco ) የሚባለው የማኅተም ማኅበር በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. የቀድሞውን እትም አድሶ በማተም እንደገና አራብቶታል ። ስለጋላ ታሪክ የሚከታተል ሁሉ በዚሁ ተመርቶ ጽሑፉን ቢያነበው መልካም ነው ።


ግዕዙ ነገደ ዮቅጣን የሚላቸው ለአሁኑ ለአማራና ለትግሬ የነገድ አባት የሆኑት የሴም ልዩ ልዩ ነገዶች አመጣጣቸው በብዛት ከደቡብ ዓረብ መሆኑ በብዙ ጸሐፊዎች ዘንድ ተመርምሮ ሲታወቅ የጋሎች ግን በዚህ በልብነ ድንግልና በገላውዴዎስ ጊዜ ከዛሬው የሱማሌ ረፑብሊክ አውራጃ እየተነሡ ወደ ደቡቡና ወደ መካከል ኢትዮጵያ መግባታቸውን እንጂ በሱማሌ አገር የነበሩት በመዠመሪያ ከየትኛው ክፍለ ዓለም መጥተው መሆኑን አጣርቶ በማስረጃ ያቀረበልን ስለሌለ ስለ ሥረ ነገዳቸው በትክክል መናገር ችግር ነው ።

አለቃ ታየ በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ መጽሐፋቸው ጋሎች ከእስያ ፈልቀው በማዳጋስካርና በኬንያ በኩል መጥተው ቦባሳ ደርሰው ከዚያ የገናሌን ወንዝ ተከትለው . . . . . . በየዘመኑ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ገብተው እንደኖሩ ከዚያ በዛጐዬዎች ጊዜ በጠጠውድም (፩ሺ - ሺ፶፩ ዓ. ም.) ና ባዬ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (፲፫፻፯ - ፲፫፻፴፯) ዓ. ም. ወደላይ እየገፉ እየተዋጉም እየገበሩም ይኖሩ እንደ ነበሩ ጽፈዋል (1) ። ነገር ግን ባለታሪኮች አሉ ከማለት በቀር ይኸን የታሪክ ምንጭ ያገኙበትን ለይተው ስለአልጠቀሱ በተለይ ከእስያ ፈልቀው በማዳጋስካር በኩል ለመምጣታቸው በማስረጃ ስለአልተደገፈ የታሪክ መደምደሚያ አድርጎ ለመቀበል ቢቸግርም አጻጻፋቸው ከአባ ባሕርይ ጽሑፍ ጋር ስለሚመሳሰል ዋጋ ያለው ነው ። በቅርቡ ግን እነሣሣቸውና የነበሩበት ሥፍራ ቀድሞ የእንግሊዝና የኢጣልያ ሱማሌ ይባል ከነበረው ጐን መሆኑን ጽሑፉ ያመለክታል ። ቤርሙዴዝም ወደፊት እንደምናነበው በወሬ እንደሰማው የጋሎች አገራቸው ሞጋዶክሶ (ሞቃዲሾ) ጐን ነው ይላል (2) ። እንደዚሁም የጋሎች ተግባራቸውና ነገዳቸው የጊኔን አገር ከወረሩት ከሱምባ (ግኔዝ) ጋር መመሳሰሉን ይጠቅሳል ። ምናልባት እነዚያም እነዚህም ከእንዶኔዝያ ፈልቀው ግማሾቹ ወደ ኢትዮጵያ የቀሩት ወደ ጊኔ ቢሳዎ ሄደው ፖርቱጋል ይኸን ወረዳ ከመያዙ በፊት ወረው ይሆናል ።

(1) የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ - አለቃ ታዬ - ገጽ 38 - 40

(2) Histoire du christianisme ገጽ 216


## ከፍ ላይ የሚገኝ




ISIC

(1) —
(2) —
(3) —
(4) —ዡ መሪያ የነገድ አባት ስ፡
(5) —ጆች ወለበሎ የሚቆጥራ
(6) —ን በወረት ጊዜ ስድስተ
።


## አባ ባሕርይ ጽ




### የአባ ባሕርይ ማመልከቻ

(1) — የጅሌ ነገዶች ኢላ አቦ ልኢስ ከብሃታቸው የተነሣ ቱለማ ተብለዋል ።
(2) — የጅዳ ነገዶች ሊበን ጉድሩ ሁለቱ ከወንድማቸው ከሐካኮ ተለይተው በቦረን አምቢላ የሹመት ዘወ
(3) — የጅዳ ልጅ ሐካኮ ከደአሊ ልጆች ከአቦና ከሱባ ጋር ተስማምተው ቢርመጅ ተብሎ በተሠየመው በ
(4) — የአቦ ልጆች ሲስማሙ በሩቁ የነገዳቸው አባት ስም ሜጫ ይባላሉ ሲጣሉ ግን በቅርቦቹ የአፍሬና የሲ
(5) — የጋላ ነገድ ቦረይቱማና ቦረን ከማለት በቀር ቦረን የበረይቱማ ወንድም መሆኑን ወይም የሰዲራ የ
(6) — ሦስቱ የወሎ ልጆች ወረ ቡኮ ወረ ጉራእ ወረ ኖሌኢሉ በአባታቸው ስም ወሎ ይባላሉ ። የቀሩት ሦ
ዜና ጋላ የሚባለው የአባ ባሕርይ መጽሐፍ ጉይዲ ያሳተመው ። CORPUSCO ያሳደሰው

መጽሐፍ ላይ የሚገኝ የጋሎች የዘር ግንድ ።




በመዠመሪያ የነገድ አባት ስም ሰኢራ ይባላሉ ።
ልጆች ወለ ብሎ የሚቆጥራቸው ፲፩ ብቻ ነው ።
ጉጽያን በወረሩበት ጊዜ ስድስቱም ባንድነት ተሰማሙ ።
ነ አለ ።

ISIC

አባ ባሕርይ በመጽሐፋቸው በመዠመሪያው ክፍል ጋላ ከምዕራብ በኩል ፍና ከሚባለው ከባሌ ከሚዋሰነው ካገሩ ወንዝ ተሻግሮ በወናግ ሰገድ ዘመን ጣ ብለው ይዠምራሉ ። ነገር ግን የመጡበት የአፍሪካ ቀንድ ወይም የሱማሌ ገር ለባሌ ምሥራቅ የቀረው ቢቀር ምሥራቅ ደቡብ ሲሆን ፤ ምዕራብ ያሉበት ክንያት አይገባኝም ። ከቦረና ግድም እንደሆነ የመጡት ባሌ ለቦረና ሰሜኑ ነው ።

ጸሐፊው አባ ባሕርይ በዓፄ ወናግ ሰገድ ዘመን ጋላ መጣ ሲሉ ዓመተ ምሕረ ፣ን ስለ አልጠቀሱ ከግራኝ በፊት እንደሆነ የዓፄ ልብነ ድንግል ዜና መዋዕል ከአዳ ቶቹ መሪ ከማኅፉዝ ጋር ከመዋጋታቸው በቀር አንድ ጊዜም ከጋላ ተዋጉ የሚል ፃሐፍ አላጋጠመኝም ። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን አመጣጣቸው በሰላም እየገበሩ ላመቀመጥ መጠናቸውም ያነሰ ሊሆን ይችላል ። ከግራኝ እነሣሥ በኋላ እንደሆነ ግን ግራኝ ከተነሣበት ከ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ በዝርዝር እንዳነበብነው ሁሉ ንጉሡ እስኪሞቱ ድረስ ግራኝ የወጋቸው የአዳልን የሱማሌን በዙሪያው ያለውን ልዩ ልዩ ነገድ ይዞ በእስላምነቱ ወይም ሀብት ፍለጋ ሲረዱት የመጡትን ቱርኮችን ዓረቦችን ፤ ፋርሶችን ፤ ሕንዶችን ይዞ ነው እንጂ በኛም በታሪክ ነገሥቱ በዓረብ ፋቂህም ውስጥ ከግራኝም ጋር ሆነውም በቀጥታ ለብቻቸውም ጋሎች ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ተዋጉ የሚል ጽሑፍ አይገኝም ።

ይኸንንም የምንለው በብዛት በራሳቸው ስም አለመምጣታቸውንና አለመዋ ጋታቸውን እንጂ ከጋላ ነገድ ውስጥ ከወዲህም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ከወ ዲያም ከግራኝ ጋራ አልነበረም ማለት አይቻልም ። በግራኝ የጦርነት ሰዓት ሁሉ አረቦች አዳሎች ሱማሌዎች በብዛት ከግራኝ ጋር ቢሆኑም ከወዲህም እነዚሁ ነገ ዶች ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ክርስትና እየተነሡ ምናልባትም የእስላም ሃይማኖታ ቸውን እንደያዙ ወይም ያለሃይማኖት በሹመትም በሎሌነትም ተቀምጠው ከግራኝ ጦር ጋር መዋጋታቸው የማይቀር ነው ። የግዕዙ ታሪክ ነገሥት የጋሎችን ባዔ ገላው ዴዎስ ዘመን መምጣት ሲተርክ በግራኝ ጊዜ ከግራኝም ወገን ባዔ ልብነ ድንግል ጐራም መሠለፋቸውን እያወሳም ። ሌላ ቀደም ብሎ በአማርኛ የተጻፈ ጽሑፍ ግራኝ በተነሣና ጦራቸውን ባሸነፈ ጊዜ ንጉሡ ቱሉ የሚባል አጋፋሪ ነበራቸውና «የቀረው ቢፈራ ቱሉ እንዴት ፈራ» አሉ የሚል አለ ። ስለዚህ ምናልባትም አለቃ ታዬ እንዳሉት በጠጠውድም (፲፮ኛ መቶ ዓመት) ጊዜና ባዔ ዓምደ ጽዮን ዘመን (፲፬ኛ መቶ ዓመት) በመጠኑ መጥተው ሳለ አሁን በገላውዴዎስ ጊዜ በብዛት ወር ረው ይሆናል ።

በዚሁ ዓይነት ጋሎች በጋላ ስም ሳይሆን በሌላ የነገድ ሥያሜ እየተጠሩ ቍጥ ራቸው ቢያንስም ከልብነ ድንግል በፊት ባለው ዘመን ሁሉ ይኸውም ማለት በሱ ማሌ አገር በተቀመጡበት ጊዜ ሁሉ በኢትዮጵያ ምድርም በቤተ መንግሥቱም መኖራቸው የማይቀር ነው ።

ስለነገዳቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከአባ ባሕርይ ለየት አድርገው ከረዩ የቱለማ የሜጫ የወሎ አባት ላሎ ባዔ ዓምደ ጽዮን ዘመን በፈጠጋርና በደዋሮ እን ደነበር ጽፈዋል ። ከዚሁ አያይዘው ባዔ ዓምደ ጽዮን ዘመን በእጨጌ ፊልጶስ እርግ

ማን ረኃብ በሀገር በተነሣበት ጊዜ አንዲት የፈጠጋር ወይዘሮ ወደ ደዋሮ ሄዳ የአዝማች እንድርያስ የላም ራስ ባርያ ለነበረው ላሎ ለሚባለው ወተት እንዲያጠጣት መግባቷን እርሱም ሚስት አድርጎ አስቀምጧት አራት ወንዶች ሦስት ሴቶች ልጆች እንደወለደችለት ፤ የወንዶቹ ስም ከረዩ ቱለማ ሜጫ ወሎ የሴቶቹ ስም አልኮ ዱረቲ አያንቱ መሆናቸውን ጽፈዋል ። ይኸም ጋሎች ባዔ ዓምደ ጽዮን ዘመን (፲፫፻፺ - ፲፫፻፴፺ ዓ. ም.) መኖራቸውን ያስረዳል ። ከዚሁ አያይዘው የግራኝ ጦርነት የተነሣበትን ሲያትቱ ላሎ ከጌታው ከእንድርያስ ቢጣላ ዖዳ ነቢ ለሚባል የጋላ ጠንቋይ ነግሮ በርሱ ምክር በግና ፍየል ወይፈን አርዶ ደማቸውን በግንባሩና በፈረሱ ግንባር ላይ ቀብቶ ቢዋጋ ማሸነፉን ፤ እነዚህም የላሎ ነገዶች በርከተው እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ደርሰው ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ንጉሡ በነዚህ ልማድ በመዋጥ የመስቀል ለት እንደ ጋሎች ልማድ ፈረሳቸውን ደም ቀብተው ትምባሆ እየጠጡ . . . ቦካን ጦር አውርድ እያሉ መሬት መደብደባቸውን ጽፈዋል (1) ። ይኸም በመሠረቱ ከዚህ በፊት በምዕራፍ ፳፮ ላይ እንዳተትነው ከእውነት የራቀ ቢሆንም ባዔ ልብነ ድንግል ዘመን የጋሎችን በብዛት መኖር ያሳያል ። እንደዚህ ሆነው እዚያም እዚህም ያሉት በሰላም ሲኖሩ አሁን ግን ያዔ ልብነ ድንግልና ያዔ ገላውዴዎስን ክርስቲያናዊ መንግሥት ግራኝ ካደከመው በኋላ የደከመውን እየወጉ ከበረሀማው አገር ወደ ለምለሙ አገር ለመዝለቅ የወረራ ጊዜና ወቅት አማርጠው ተነሥተው ይሆናል [sic] ይኸንንም ጊዜ በትዕግሥት እየጠበቁ የበረሃውን የችግር ኑር ችለው ተቀምጠዋል ማለት ነው ። ምናልባት ያን ጊዜም በመካከላቸው እንደ አባ መቻል አብቴ ያለ ምክር ዓዋቂ ይገኝ ይሆናል ።

በጦርነት አነሣሣቸውን ለመዠመሪያ ጊዜ ታሪከ ነገሥቱ የሚተርከው በዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን ስለሆነ ምናልባት በዚያ በብዛት በነበሩበት ቀድሞ የኢጣልያና የእንግሊዝ ሱማሌ ይባል በነበረው አውራጃ አሁን የሱማሌ ሬፑብሊክ ከሆነው ከሱማሌዎች ጐን ሲኖሩ በጣም ዘራቸው በርከቶ አገር ጠቧቸው ሳለ አሁን ግን እላይ እንዳልነው የግራኝ ጦር በተለይ ክርስቲያናዊውን ሕዝብ በመውጋት ስለአዳከመው ምቹ ጊዜ መርጠው ባዔ ገላውዴዎስ ጊዜ በብዛት ባንድ ወገን የዋቢ ሸበሌን በሌላ ወገን የነገሌን ወንዝ እየተሻገሩ መምጣታቸው ሳይሆን አይቀርምና የጊዜው ምርጫና የጦርነቱ ዘዴ መንገድ ያለው ነው ። ከወዲያም ግራኝ ለመውረር በሚዘጋጅበት ጊዜ ባንድ ዘመን ተነሥተው ከርሱ ጋር ከመጣላት የርሱን ፍጻሜ በምክርና በትዕግሥት ተጠባብቀው እርሱ ሲሞት በአሁኑ በዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን ተነሥተው ደዋሮን ባሌን መውረር ዠመሩ ማለት ነው ። በገላውዴዎስም ዘመን ንጉሡ ራሳቸው ቤርሙዴዝ ወደፊት ሲተርክ እንደምናየው በምዕራብ በኩል ወደ ጋፋት በዘመቱበትና በሰሜን በኩል ለተነሣው የቱርክ ኃይል ወታደራቸው ተከፍሎ የሄደበት ጊዜ በመሆኑ በማናቸውም ረገድ ጊዜውና አጋጣሚው ምክንያት ሁሉ ለጋሎች ወረራ የተመቸ ነበር ።

(1) ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 29 - 31

አባ ባሕርይ በመጽሐፋቸው ላይ የጋላን ነገድ የተቻላቸውን ያህል ሲዘረዝሩ የጋሎች የዘር ግንዶች በረይቱማና ሰጺራ የሚባሉት መሆናቸውን በረይቱማ ከረዩን መረዋን ኢቱን አከቱን ወረንጢሻን ሁምባናን ከወለደ በኋላ ከረዩ ሊበንን ፤ ወሎን ፤ ጅሌን ፤ አቦን ፤ ሱባን ፤ በላዕን ይወልዳል ። ወሎ ደግሞ በፈንታው ወረቡ ኮን ፤ ወረ ጉራእን ፤ ወረ ኖሌኤሎን ፤ ወረ ከረዩን ፤ ወረ አሊን ፤ ወረ ኖሌአሊን መውለዱን ከጻፉ በኋላ ሦስቱ የመገኘመሪያዎቹ በወሎ ስም እንደሚጠሩ ሦስቱ የመጨረሻዎቹ ሰዴቻ ሲባሉ ቆይተው በኋላ አቦሊ ከሚባለው ከቤተ መንግሥት ሰው ጋር ተዋግተው እርሱን ከገደሉ በኋላ በርሱ ደም ታርቀው መስማማታቸውን ያመለክታሉ (1) ።

ባንድ ወገን ደግሞ ሰጺራ ዳጨን ፤ ዳጨ መጫን (2) ፤ መጫ ጅዳንና ዶአሌን ይወልዳል ። ጅዳ ደግሞ ሊበንን ጉድሩን ሐካኮን ሦስቱን ሊበን አምዩን ዋሊሶን ኩታዩን (3) ጉድሩ ሲርባን መሉልን ጨረቃን ፤ ሐካኮ አቦን ሐርሱን ሊሙን ይወልዳል ። የሊበንና የጉድሩ ነገዶች ከወንድሞቻቸው ከሐካኮ ልጆች ተለይተው በቦረን እምቢሳ የሹመት (ሉባ) ዘመን አፍሬ በበርቱማ ጊዜ ሮበሌ መባላቸውን የሐካኮ ልጆች ደግሞ ከዶአሊ ልጆች ከአቦና ከሱባ በመስማማት ቢርመጅ ተብሎ በተሾመው በሉባ ዘመን ሰዴቻ መባላቸውን ይገልጻሉ ።

የመጫ ሁለተኛው ልጅ ይኸውም ማለት የጅዳ ወንድም ዶአሌ ሆኮን ጭሌን አቦን ሱባን ሲወልድ ሆኮ ኪረሞን እመሩን ጂዲን (4) ይወ፲ለ፬ል ።

ባንድ ወገን ቦረን የሰጺራ ወይም የዳጨ ልጅ መሆኑን የአባ ባሕርይ መጽሐፍ አይገልጽም ። ፲፪ ልጅ መውለዱን ያወሳና የሚቆጥራቸው ፲፩ ብቻ ናቸው ። የነርሱም ስም ዳጨ ፤ ጅሌ ፤ ሆኮ ፤ በቾ ፤ አቦ ፤ ሐካኮ ፤ ሱባ ፤ እነዚህ ሦስቱ ሰዴቻ ይባላሉ ። ጭሌ ፤ ሊበን ፤ ጉድሩ ሆኮ እነዚህ አራቱ ደግሞ አፍሬ ይባላሉ ። በድምሩ ፲፩ መሆናቸው ነው ።

የአቦ ልጆች ሰዮ አቦኖ ፤ ቱምኤ ሲስማሙ በሩቁ የነገድ አባት ስም መጫ (ሚጫ) ይባላሉ ። ሲጣሉ ግን በቅርቦቹ የአፍሬና የሰዴቻ (በሉባ የሹመት ስም) ወገን ይባላሉ ። ሁሉም ባንድነት ከቱለማ ወገኖች (የጅሌ ነገዶች) የተስማሙ እንደሆነ በመጀመሪያው የነገድ አባት ስም ሰጺራ እየተባሉ ይጠራሉ ። የአቦ ወንድም ሱባ ሐገለባቦንና ጩራን ይወልዳል (5) ።

የጋላ ነገድ እንደ እስላሞችም መሪያቸውን ሱልጣን ወይም ይማም አለዚያም ኤሚር ብለው ለዘለቄታ አይሾሙም ። እንደኛም እንደ ክርስቲያኖቹ ከአንዱ ነገድ የተሻለውን መርጠው በማንገሥ የዘለቄታ ገዥ አያደርጉትም ። ነገር ግን እንደዛሬ

(1) Hist. genti galla. Guidi. ገጽ 224

(2) በዛሬ አጠራር ሜጫ

(3) በዛሬ አጠራር ወሊሶና አማያ ኩታዩ

(4) የአያቱን ወንድም ስም ወርሏል ማለት ነው ።

(5) ክፍል 2 ገጽ 223 - 224

ዘመን የሬፑብሊክ አገዛዝ በየስምንት ዓመት ውስጥ ከየነገዱ እየተመረጡ ቱለማ ፣ አፍሬ ፣ ሰዴቻ ፣ ቢርመጅ ዳዌ እየተባሉ በነርሱ አጠራር ሉባ የሚባለውን ሹመት ይዘው በየበኩላቸው ስለሚዘምቱ የመጠሪያ ስማቸውንና የሉባነት ስማቸውን እየ ለያዩ ለማቅረብ አንዳንድ ጊዜ ይቸግራል ። የግማሾቹን ቢቻል የጠቅላላውን አይ ቻልም ።

ይህ የሉባ ሥያሜ አባ ባሕርይ እንዳመለከቱት በክርስቲያኖቹ ነገሥታት ዘንድ የጦር ሠራዊቱ ድርጅት በየክፍሉ በፀር ዋጀት በድል ደመና በፀር ሾተል አዳል መብረቅ ፣ ዣን አሞራ በጥረ አሞራ (በትረ አሞራ ?) የሚባሉ እንደነበሩ ያዔ ዘርዓ ያዕቆብና ያዔ በዕደ ማርያም ዜና መዋዕል እንደሚያመለክተው በዚህም ባዔ ልብነ ድንግልና ባዔ ገላውዴዎስ ዘመን በድል ፀሐይ ሥሉስ ኃይሌ ፣ ጊዮርጊስ ኃይሌ እየተባሉ የሚጠሩ የመንግሥት የክፍል ጦር ሠራዊት እንደነበሩና የሉባዎች ሹመት ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይነቱን አባ ባሕርይ ጨምረው ገልጸዋል (1) ።

ይኸን የመሰለው የጠቅላላ ወታደር ስም እንደፈረሰ ስም እየገነነ በቀን ብዛት ያንድ ተዋጊ መጠሪያ ስም እየመሰለ እገሌ እንደዚህ አድርጎ ሞተ ይባላል ። ይኸም ስያሜ በኛም በጋሎቹም ዘንድ የሉባው ሥያሜና የወታደር ስም የሠፈሩበት ወይም የተተከሉበት አገር የነርሱን ስም ይዞ ቀርቷል ። ብዙ ጊዜም እንደ ሜጫ እንደ ወሎ እንደ ሊበን እንደ በቾ እንደ ሰዮ ያሉት የወረዳ አገሮች የጋሎቹን የአባ ቶቻቸውን መጠሪያ ስም ወርሰው እስከዛሬ ያገር ስም ሆነው የሚጠሩ አሉ ። እነ ዚህ አገሮች ደግሞ ከጋሎች ወረራ በፊት በግዕዝ በተጻፈው ጽሑፍ ላይ የቀድሞ ውን ስም እየጠራ ስለሚገኝ የፊተኛውን አጠራር ከኋለኛው ሥያሜ ጋር ማገናዘቡ ማስቸገሩን በየጦርነቱ ምዕራፎች ባለፈው አመልክተናል ።

ISIC

ለምሳሌ የአዲስ አበባ ከተማ ያለበትና አካባቢው እንዶጥና ይባል ነበር ። በኋ ለኛው ጊዜ ፊንፊኔ ፣ ጉለሌ ፣ የካ ፣ ፉሪ የሚባል የጋልኛ ሥያሜ ወጣለት ፣ የዛሬው የየረርና የከረዩ አውራጃ ግዛት ፊጠጋር ደዋሮ የሰላሌ ግዛት ግራርያ የአዲስ ዓለም አካባቢ አበቤ ሜታ የሚባለው ቀድሞ እንደ ገብጣን የዛሬው የወሎ ጠቅላይ ግዛት በፊት ቤተ እምሐራ ይባል እንደነበረ ከዚህ በፊት በየምክንያቱ አመልክተ ናል ። አሁን ጋሎች ያደረጉትን ጦርነት በመጠኑ እንመልከት ።

(1) ወይሠመዩ አስማቲሆሙ በበነገዶሙ ወዓልቦሙ ንጉሥ ወኢእግዚእ ከመ ካልእ ሕዝብ አላ ይት ኤዘዙ በሉባ እስከ ፰ ዓመት ወድኅረ ፰ቱ ዓመት ይሠየም ካልእ ሉባ ወይሠዓር ቀዳማዊ . . . . . . እስመ ሶበ ይሠዓር ሉባ ያወጽኡ ስመ ለርእሶሙ በረይቱማ ወቦረን በከመ ይሠመዩ ሐራ ንጉሥ ሥሉስ ኃይሌ ፣ በድል ፀሐይ . . . . . . ክፍል አራት ።

## ምዕራፍ ፲፯

## ስለጋሎች ጦርነት በአባ ባሕርይና በቤርሙዴዝ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ማስረጃ

ያህል ዓፄ ገላውዴዎስ በአማራውና በትግሬው ወረዳ ያለውን አገር የተቻላቸውን ከአስለቀቁም ከአደላደሉ በኋላ በተለይ ሰፊውን የደቡቡን ክፍል ለማስለቀቅም ማድረጋቸውን በኋላ ለመቆጣጠር እንዲመች መቀመጫ ከተማቸውን በወጅ የሚያ ታሪከ ነገሥቱ ያወሳል ። በዚህም ከሶርያ ከፈረንጅ አገር በመጡ ጥበበኞች ማንብና ማምር ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ ረዥም ተመል የሚያስደስት አትክልት ሁሉ አስተክለው በዚያ መቀመጣቸውን ፤ ከዚያም አሠር ሰው ግራኝ የአቃጠለውን የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሳምረው አሰቃና ተው ቅዳሴ ቤቱ ተከብሮ ሹም ሽር በተደረገበት ሰዓት የሠራዊት ጠቅላይ ሰጥ ታላቁ ካህን ለተባለው ለአፈወ ድንግል በወርቅና በዕንቊ የተሠራ አክሊል ያመለከ ተው የንጉሥ ልብስ አልብሰው በታላቅ ሹመትና ሽልማት እንዳከበሩት የተሾመ ታል ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ሥራው አልቆ የተመረቀበትና አፈወ ድንግል የገምቦ በት ዓመት ፲፭፻፵፩ ዓ. ም. መሆኑን ይገልጽና በሌላ ምዕራፍ ላይ ደግሞ እንዳሳ ሕዝብ ከዚያ የገባ ሕዝብ የጉመር ሕዝብ አልገዛም ብሎ ፫ ወር ተዋግተው መስ መኑ በዚሁ ጦርነት መካከል እስላሞች ተነሥተው በክረምቱ ወራት አንድ መሪ ፍን በበጋው ወራት የተድባበ ማርያም አለቃና የጦር ሠራዊቱ ስመ ጥር ጎዘን አፈወ ድንግል መሞታቸውን ፤ በዚህም ሁኔታ ንጉሡ ገላውዴዎስ መሪር ጋሎቹ እንደተሰማቸውና ይኸን ከማየት ሞትን እንደተመኙ ካመለከተ በኋላ ወደ ጦርነት ይመጣል (1) ።

ታሪከ ነገሥቱ እና አፈወ ድንግል በሞቱ በሁለተኛው ዓመት ንጉሡ ጋሎቹ ወደ አሉበት ቀበሌ ሄደው መዋጋታቸውን በዚያም ግማሾቹን በሰይፍ ገድለው የቀ ሩትን ታዛዥ ገባር እንዳደረጓቸው ከዚያ ወዲያ ከጋላ ጋር መዋጋት እንደቆመ ፤ ጋሎ ቹም እንደገና ቢመጡም በድብቅ እንጂ በገሃድ መጥተው አለመዋጋታቸውን ባንድ ምዕራፍ ላይ ካመለከተ በኋላ በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ የጋሎቹን አጥቂነትና ጋሎቹ ለአሳደዷቸው ክርስቲያኖች መኖሪያ የሚሆን ከተማ ያሠሩ እንደነበረ ስለ ሚተርከ የጋሎቹ ጦርነት ባንድ ጊዜ ጦርነትና በቀላሉ አለመቆሙን እንረዳለን (2) ከዚህ በፊት የቱርኮችን ጦርነት አመለከትነው ላይ ዐንጉሡ ባንድ ወገን ስለ ሃይማ

(1) . . . . . . ወበ፲፻ወ፭፻፵ወ፩ እምትሥጉተ እግዚእነ ክርስቶስ . . . . . ሤሞ ማር ገላውዴዎስ ሊቀ ሳዕለ ካሀናት ኅሩያን ለካህን ዓቢይ አፈወ ድንግል ወመልአ ሎቱ እዴ እንዘ ይኬልሎ በአክሊለ መንግሥት ዘእም ወርቅ ጽሩይ ወላዕሌሁ አእናቍ ሊሉያነ ኅብር ወአልበሶ አልባሰ ንጉሣዌ . . . . ወበእማንቱ አዝማን ተንሥኡ ዘመደ ተንባላት በመዋዕለ ክረምት ቀተልዎ ለአሐዱ መስፍን ምስለ ሠራዊቱ ። ወበመዋዕለ ሐጋይ ካዕበ ቀተልዎ ለአፈወ ድንግል ዓቢየ ቤተ ክርስቲያን . . . . . ወላዕለ ኵሉ ዝንቱ ኢኮነ መርምመ ንጉሥ ገላውዴዎስ አላ የኃዝን ወይፈቱ ይሙት እም ይትሐ ገጽ 52 ፡ 53 ፡፡ 59 ፡ 60 ፤
ጐል ኵሉ ሕዝብ ። ጉንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕላቸው

(2) ወለውእቱ ዘመነ ረሰዮ ንጉሥ ክቡር ላዕለ አስተሕምሞ ፈሊጠ ሀገረ ምስካይ በእንተ ሰብእ ምዕ መናን እለ ተሰዱ እምጋላ ወውሂበ መፍቅዳቲሆሙ ። ገጽ 91 ፤

ISIC

ኖት ክርክር በሌላው ወገን በሰሜን በኩል ስለመጡት ቱርኮች ውጊያ እያሰቡ ቀጥሎ ከፊተኛው ውጊያ የተረፉት ጋሎች እንደገና አገር እንዳያጠፉ ይጨነቁ ነበር» ያለውን መልሰን እናስታውሳለን (1) ።

በበኩላቸው አባ ባሕርይ በመጽሐፋቸው በክፍል ፱ ዳዊ የሚባለው የቦረን ወገን በመዠመሪያ ከአዝማች ፋሲል ጋር ተዋግቶ እንዳሸነፈና ፋሲል እንደሞተ ከዚያ አከታትሎ በጥረ አምራንና ወጅን እንዳጠፋ ፤ ማልባህ የሚባለው በባሌ እን ደተዋጋ በክፍል ፲ ሉባ ኪሎሌ አዳል መብረቅ የሚባለውን የደዋሮ ቆላን ጦር ተዋ ግቶ እንደ አጠፋው ፤ በክፍል ፳ ቢፎሌ ደዋሮን በሙሉ ቀጥሎ ፈጠጋርን ሁሉ ወርሮ ሕዝቡን ማርኮ እንዳስገበረ ፤ ይኸም ነገድ ከበግና ከፍየል በቀር ሰውን ወንዱ ንም ሴቱንም ከብቱን ሁሉ እንደገደለ ፤ ምስሌ (ምችሌ) ደግሞ ዣን አምራን ከፈጀ በኋላ ደጎ ላይ ከሐመልማል (2) ጋር አሣ ዘነብ ላይ ከራሳቸው ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር መዋጋቱን በዘጠነኛው ክፍል ስለሚገልጽ እላይ ታሪክ ነገሥቱ ቀለል አድርጎ ያቀረበው አሁንም አባ ባሕርይ ጠቅሰው ያለፉት ምዕራፍ ጦርነቱ በዝርዝር ተጽፎ ቢገኝ ኖሮ አንድ መጽሐፍ የሚወጣው ይሆን ነበር ፤ ይህ የጋሎች ጦርነት ብዙ ሰው ከሁለቱም ወገን የተላለቀበት ብዙ ጊዜ የፈጀ በያለበት በብዙ ቦታ ታላላቅ ጦርነት የተደረገበት መሆኑ ይታወቃል ። የሆነ ሆኖ ወደፊት ደግሞ እንደምናነ በው በድል ወንበራም በራሱም ምኞት ተገፋፍቶ የሙጃሂድ ልጅ ኑር መጥቶ ዓፄ ገላውዴዎስን ወግቶ ድል አድርጎ [illegible]ቅላታቸውን አስቆርጦ በደስታ ወደ ሐረር ሊመለስ ሲል ይኸው ምስሌ (ምችሌ) ተብሎ የተሠየመው ፭ኛው ሉባ አዘሎ በሚ ባለው አቅራቢያ ተዋግቶ ከሠራዊቱ የሚበዛውን እንዳጠፋበት ጋሎች ከወጡ ዝምሮ የዚያን ጊዜ ያህል ሠራዊት (የኑር) እንዳላለቀ . . . . . በዚህም ጦርነት በወጅ ኑር ያፈሰሰውን የክርስቲያን ደም እግዚአብሔር ብድራት እንደመለሰ መነ ኵሴው ደራሲ ጽፈዋል (3) ። በዚህ ዓይነት የጋሎች ጦርነት እነሣሥ ከነርሱ ሃይማ ኖትና ልማድ የተለየውን የእስላምንና የክርስቲያንን ሕዝብ እያጠቁ በእነዚህ እጅ ያለውን አውራጃ ብቻ ለማግኘት እንደሆነ ይታያል ። ምናልባት ቀደም ብለው ጋሎቹ እነፋሲልን ፥ እነሐመልማልን ፣ እነአፈወ ድንግልን ሲያጠቁ እስላሞቹ ተደ

(1) ታሪክ ነገሥት ገጽ 108

(2) ሐመልማል ያፄ ልብነ ድንግል እኅት የወይዘሮ ወለተ ቀለምሲስ ልጅ ነው ። ከጋሎች ጋር በተዋ ጋበት ላይ አባ ባሕርይ የሞተ አስመስለውታል ። ነገር ግን ታሪክ ነገሥቱ ከአፈወ ድንግል ጋር አንድ መስፍን መሞቱን ስለሚናገር ሐመልማል መሆኑን አይለይም ። ነገር ግን ይኸው ሐመል ማል ይሁን ወይም ሌላ ይሁን ባፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን ሸፍቶ አስቸግሮ እንደነበረ ዜና መዋዕላ ቸው ይገልጻል ። ገጽ 15 - 20 ።

(3) ወዳዊ ዘአጥፍኦ ለበጥረ (በትረ) አሞራ እምሰብአ ቦረን ውእቱ . . . . . . . ወወረደ በሙ ፋሲል ወቀተልዎ . . . . . ወሳልስ ሉባ ተሰምየ ኪሎሌ ውእቱ ፀብዖሙ ለቆላተ ደዋሮ ዘስሙ አዳል መብረቅ ወሀምስ ሉባ ተሰምየ ምስሌ ወውእቱ ዘቀተሎ ለዣን አሞራ ወተጻብዖ ለሐመልማል በደጎ ወአጥፍኦሙ . . . . . ወአመ ይወርድ ኑር ሀገሮ ውእቱ ተራከቦ በቅሩበ ሀዘሎ ወቀተለ መብ ዝኀቶሙ . . . . . እስመ ፈደዮሙ እግዚአብሔር በቀለ ደሞሙ ለአግብርቲሁ ዘከዓዉ በወጅ . . . . .

እንደ አባ ባሕ
ነተው አሁን ደግሞ በአዘሎ ጦርነት ኑርን ስላጠቁ ክርስቲያኖቹ
ርይ ተደስተዋል ማለት ነው (1) ።

የጋሎቹ አነሣሥ በረኸርም የጦር ግንባር ከብዙ ቦታ ገንፍሎ የተገሠመረ ጦር ነት ስለሆነ ባንድ ጊዜ ወይም በጥቂት ዓመታት ሳይወሰን ነዋሪነታቸውንና መብ ታቸውን በነዓዬ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት እስኪያረጋግጡ ፤ ሰፋፊውን አገር ይዘው ባለቤት እስኪሆኑ ድረስ ጦርነቱ ባፄ ገላውዴዎስም ባፄ ሚናስና በነዓፄ ሠርፀ ድንግልም ዘመን እንደቀጠለ ነበር ። ከሱስንዮስም ወዲህ አልፎ አልፎ ጦር ነቱ አልቆመም ነበር ። ነገር ግን ከ፲፰ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ያለው የመጨረሻው ጦርነት ያው አማራውም ሌላውም ነገድ አልፎ አልፎ ከሚያነሣው ከተለመደ የው ስጥ ጦርነት ወይም ክርስ በርስ ከተለመደ ግጭት የሚቆጠር ነው ።

የዚህን ያፄ ገላውዴዎስን ዘመን የጋላ ጦርነት በበኩሉ ዮሐንስ ቤርሙዴዝ ከኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ላይ አልፎ አልፎ ስለጋሎች የጠቀ ሰውን ባለፈው አንብበናል ። እንደ ቤርሙዴዝ አጻጻፍ ዓፄ ገላውዴዎስ ከግራኝ ሞት ወዲህ የተረፉትን የፖርቱጋል ተወላጆች በደዋሮ አገር መሬት ሰጥተው ደል ድለው አስቀምጠዋቸው ሳለ የዚህ አገር ጌታ ካሊድ የሚባል የንጉሡ የቅርብ ዘመድ የግዛቱ አበል ለፖርቱጋሎቹ በመሰጠቱ ተናዶ ከፖርቱጋሎቹ ጋር ሲዋጋ መሞቱን ፤ ይህ ሰው ከሞተ በኋላ ፖርቱጋሎቹ የአራት ወር ዕረፍት እንዳደረጉ ንጉሡ ነገሥቱ ጋሎቹ በድንገት ደዋሮን ሊወሩ አስበዋል ማለትን ሰምተው ፖርቱ ጋሎቹን ለውጊያ ተዘጋጁ ብለው እንደ አዘዟቸው ይገልጽና የጋሎቹ አገር በሞቃ ዲሽ ጐን መሆኑን እነሱም ጨካኞች ከመሆናቸው የተነሣ በጐናቸው ያለውን ጐረ ቤታቸውን (ሱማሌን ፤ ወይም የኬንያን ሕዝብ ?) ብቻ ሳይሆን አገሩን ምድረ በዳ ለማድረግ ሌላውንም አገር እንደሚወጉ ትልልቁን ሰው ወንዱንም ሴቱንም ከገ ደሉ በኋላ ወጣቱን እንደሚሰልቡ እነሱም በሚያደርጉት የጭካኔ ሥራ የጊኔን አገር በሙሉ ካጠፉት ሱይምባ ከሚባሉት ጋር መመሳሰላቸውን የነዚሁ የሱይምባ ነገ ዶች ክነዚሁ ከጋላ ነገዶች የወረደ መምሰሉን ይጽፍና ስለውጊያው እንደዚህ ይላል (2) ።

«ተዘጋጁ የሚለው የንጉሡ ትእዛዝ ከደረሰን በኋላ በማናቸውም ረገድ ተሰና ዳን ። በተለይ ዋና የምናሸንፍበት መሣሪያ በእሳት የሚተኰስ ስለሆነ በእ

(1) አዘሎ አዳል አገር ገዋኒ ወንዝ አጠገብ ያለ በሩቅ አንኮበር ሆኖ የሚታይ ተራራ ነው ። ተራራው ለጨርጨር ይቀርባል ።
(2) በፈረንሳዊ ( SUIMBAS ) ይለዋል ። በዚህ ዓይነት አጻጻፍ ሳይሆን SUMBA በኢንዶኔ ዥያ ውስጥ በሕንድ ውቅያኖስ ባሕር በኩል አንዲት ደሴት አለች ብዙ ፈረስና የቀንድ ከብት እንደ ሚገኝ እንሲክሎፔዲያው ሁሉ ያመለክታል ። ጋሎች ግማሹ በደፈናው ከእስያ ፈልሰው መጡ አንዳንዱ ከእንዶኔዢያ በማዳጋስካር በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ስለሚል ታሪኩ ይገናኝ እንደሆነ አይታወቅም ። እነዚሁ ሱምባ የሚባሉት ነገዶች በእርግጥ እንደ አው. ቀ. በ፲፭፻፵፮ ዓ. ም. ሳጥ (ተምኔ) የሚባሉትን ነገዶች አሸንፈው የሞንሮቭያን ፤ የጊኒ ቢዛዎንና የኮናክሪን የባሕር ደሴ ቶች መውረራቸው ፤ እነሱም አንዳንድ ጊዜ ማኔዝ መባላቸውን ጸሐፊዎች ያመለክታሉ ።
Histoire generale de l'Afrique Noire-Hubert De Champs. ገጽ 291

ገሩ ከሚገኘው ከድኝና ከከሰል ላይ ባሩድ እያዘጋጀን ለመድፋችን ጥይት አበጀን ። ለመዋጋት የማይችሉትን ሴትና ልጆች ከወረዳው እንዲወጡ ስናደርግ በዚሁ ጊዜ የጋላን ጭከና በመፍራት ብዙ የአገሩ ሀብታሞች አገራቸውን እየለቀቁ ወጡ ።

ከዚህ በኋላ ቊጥራቸው ከመጠን ያለፈ ጋሎች ወደኛ ሲመጡ አየናቸው ። ሲራመዱም ስልፍ እንደተማረ እንደ ደንበኛ ጓድ (ኤስኳድሮ) በደንብ እንጂ ዝርክርክ አልነበረም ። ወደ አጠገባችን መጥተው ሲሰፍሩ የኛ ቊጥር አነስተኛ ስለሆነ ሄደን ለመዋጋት ሳንደፍር በሠፈራችን ብቻ ሆነን ለመከላከል ወሰንን ። ቊጥራችንም ግማሹ ወደ አገሩ ተመልሶ ፤ ግማሹም በበሽታ ሞቶ ያለነው ፻፶ ፖርቱጊዞች ብንሆን ነው ። በዚያ ሆነን ንጉሡን ከመጠበቅ ጋር ፲፪ ቀን ያህል በመድፍ እየተከላከልን ቆየን ብዙም ጋሎች ገደልን ።

በመካከሉ ንጉሡም ስለአልመጡ ባሩድም ስለአለቀብን አገሩን ትተንላቸው ንጉሡን ፍለጋ ሄድን ። በበኩላቸው እነርሱም ከኛ መራቅ ፈልገው ኖሮ እኛ ስንሸሽ አልተከታተሉንም ። ከዚህ በኋላ በመንገድ ንጉሡ ደርሰው ተገናኘተን የአገሩን (ደዋሮን) መወረር ሲሰሙ ደንግጠው እንደ ሞቱ ሆኑ . . . . . . ይኸን አገርና ባሌን ሐድያን የሚያካክል ሰፊ ግዛቶች ስለተወረሩባቸው ይኸ ሁሉ የሆነው ኃጢአቱ ምን ያህል ታላቅ ቢሆን ነው ብለው አለቀሱ» ይላል (1) ።

ከዚሁ አያይዞ ከዚህ በፊት አመልክተን እንደነበረው ከፖርቱጋሎች አንዱ «ግዴለዎም አይዘኑ ነገር ግን ከ፲፭፻፲፭ርክ ቤርሙዴዝ ቢታረቁ ነገሩ ሁሉ ያምራል እኛም በርትተን እንዋጋለን ቢላቸው ለርሱ ምንም መልስ ሳይሰጡ ከዚህ በፊት ወደ አልጐበኙት አገር ለመሄድ ተከተሉኝ» ብለው እነርሱን አስከትለው እንደሄዱ ሲሄዱም ጋሎች በፊተኛው ጊዜ እንዳስለመዱት አገር ዘርፈው ወደ መጡበት ያልተመለሱ እንደሆነ በኋላ እንዋጋቸዋለን ብለው ከዚያ ቦታ በወጅ በኩል አድርገው ወደ ጉራጌ አገር መሄዳቸውንና ግብር መቀበላቸውን ከዚያ አልፈው ጋፋት ደርሰው መዋጋታቸውን ከዚያ በዳሞት አልፈው የሻንቅላውን አገር አስገብረው ባላባቱን የክርስትና አባት ሆነው ማንግታቸውን ይተርክና የጋላ ወረራ በደዋሮና በባሌ ስለጠነከረና ምንም ማድረግ ስለአልተቻለ በደዋሮ ወረዳ መሬት ተሰጥቷቸው ለነበሩት የፖርቱጋል ተወላጆች ሁሉ ብዙ ሀብትና አበል በሚገኝበት በቤተ ማርያም በአማራ አገር ለውጡን እየሰጡ እንደተከሏቸው በዝርዝር ይተርክና ቤርሙዴዝ ስለጋሎች የጻፈውን እዚህ ላይ ያቆማል (2) ።

ይሁን እንጂ ቤርሙዴዝ የሚጽፈው ራሱ የነበረበትንና ያየውን ነው ። ነገር ግን እርሱ ከደዋሮ መልስ ከዚህ በፊት እንዳነበብነው በ፲፭፻፵፯ዓ.ም. ወዳገሩ ከተመለሰ ወዲህ ንጉሡ በ፲፭፻፵፩ ዓ. ም. ከኑር ተዋግተው ሕይወታቸውን እስኪሠዉ ድረስ አራት ዓመት ያህል በዚች የጦርነት መከራ ባልተለያት አገራቸው ላይ ከፋሲል ወዲህ ሐመልማል ደጎ ላይ ታላቅ ጦርነት አድርጎ መሸነፋን የርሱን ሞት ዓፄ

(1) Histoire du Christ............. ገጽ 214 - 220
(2) Histoire du christ ............. ገጽ 220 - 248

ገላውዴዎስ በጉ-ጃም የደብረ ወርቅን ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ ሰምተው ወደባሌ
ተመልሰው ያደረጉትን ውጊያ አልጠቀሰውም ።

አባ ባሕርይ ባጭር ባጭሩ ዳዊ ፋሲልን ገደለ በጥረ አሞራን አጠፋ ፤ ሉባ
ኪሎሌ በደዋሮ አዳል መብረቅን ፤ ምስሌ (ምችሌ) ዣን አሞራን ፈጅቶ ሐመልማ
ልን ወጋ ያሉት ሁሉ እያንዳንዱ መጽሐፍ እንኳን ቢቀር ከፍ ያለ ምዕራፍ የሚይዝ
የጦርነት ታሪክ እንዳለበት አይጠረጠርም ። ነገር ግን ታሪክ በሠነድ ተንተርሶ ይዘ
ጋጃል እንጂ እንደ ግጥም ወይም እንደልብ ወለድ አይጻፍም ፤ ትንሹንም ሰነድ
በመላ አጻጻፍ ማበራከት ወደ ስሕተት እንዳያመራ መጠንቀቅ ስለአለብን አሁን
በመጠኑ የጋሎችን አነሣሥና ውጊያቸውን ካነበብን በኋላ በሚቀጥሉት ምዕራፎች
በሐረር ኑር ቤን ሙጃሂድ ያነሣውን ጦርነትና የንጉሥ ነገሥቱን አሳዛኝ አሟሟት
እንመልከት ።

ምዕራፍ ፻፶፩

የኑር ቤን ሙጃሂድ አነሣሥና ከዔ ገላውዬዎስ ጋር ለውጊያ መሰለፍ ፤

፲፭፻፶፩ - ፶፱ ዓ. ም.

ባዔ ገላውዴዎስ ዘመን ከግራኝ ውድቀት በኋላ ምንም እ1538 ብዙ ሰዎች ምሕረት
እየለመኑ ቢገቡ መጽሐፈ ቄድር ፣ መጽሐፈ ኑዛዜ እየተደገመ የሰለመው ሁሉ እን
ደገና በክርስትና እየተጠመቀ ቢመለስም በ፲፭ ዓመት ወረራ የተመሰቃቀለው አገር
ባጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ባዔ ገላውዴዎስ ሥር ኅብረት አድርጎ ባገሪቱ ላይ ሙሉ
ሰላም ሊገኝ አልቻለም ።

ምሕረት እየለመኑ ገቡ የሚላቸውም አብዛኞቹ ቀድሞ ክርስቲያን የነበሩትን
ትግሬዎችና አማሮች ወይም እነርሱን የመሳሰሉትን በኋላ የግራኝ ሥልጣንና ገዥ
ነት በገነነበት ዘመን በግዴታ ፈርተው ወይም ለመኖር ሲሉ ሰልመው የነበሩትን
ክርስቲያኖች ነው ። በተረፈ ባገር ላይ ትክለኛ ያገር ተወላጆች በአማራና በትግሬ
አገር የሚኖሩ እስላሞች አሉ ። ቀጥለው ደግሞ በአዋሽ ግራና ቀኝ የሚኖሩ የወጅ ፤
የሐድያ ፤ የባሌ ፤ የደዋሮ ሕዝቦች በላያቸው ላይ ተደባልቆ ከሚኖረው የንጉሥ
ወታደር በቀር ነዋሪው ባላገር በእስላምነትና በክርስቲያንነት መካከል ሆኖ በአረ
መኔነት የሚኖረው አብዛኛ ጊዜ ላሸናፊው ስለሚገዛ በአሁኑ ሰዓት ዓፄ ገላውዴ
ዎስ የግራኝ አሀመድ አሸናፊ ንጉሠ ነገሥት እንደመሆናቸው መጠን ራሳቸውም
እየሄዱ ጦርም እየላኩ አብዛኛው ወደርሳቸው አሜን እያለ ገብቶ ይሆናል ።

ነገር ግን እነዚያ ዓረብ ፋቂህ የሐርላህ ፣ የሀብር መጋድ ፣ የመለሳይ ፣ የሲም
የመራሂያን የኅርጎራህ የጊራ የዘርባህ ነገድ እያለ የሚጠራቸው የሱማሌና የአዳል
የኢሳ ነገዶች ከዓረብ አገር በዘይላ ወደብ በኩል መሣሪያ እየያዙ ጦርነቱን ለመካ
ፈል የመጡት የማህራ ነገዶች (ዓረቦች) ሁሉ በየአውራጃው ተበታትነው በሹመ
ትና በአበል ተደልድለው የተቀመጡት ከአገሬው በተለይ የእስላም ነክ ከሆነው

ከሐድያ ከባሌ ከደዋሮ ሕዝብ ጋር ተዋሕደው የተቀመጡት ግራኝ በወደቀበት ሰዓት በአጋማሽም ላዬ ገላውዴዎስ ቢገቡ ሌሎች ደግሞ ሳይገቡ የቀሩት ብዙዎች ናቸው ።

በዚህ መካከል በጦርነት ከሞተው ወይም በድንገት ከተማረከው በቀር የቀረው ግማሹ ሚስቱን ድል ወንበራን ተከትሎ ግማሹም በየፊናው በየአለቃው እየተመራ ወደ ሐረር መሄዱ የታወቀ ነው ። ከሄደም በኋላ ከገላውዴዎስ ጦር ጋር ውጊያ ያልቀመሰው እየተዋጋ ሸሽቶ የሄደውም እያንሰራራ በመመለስ የንጉሡን ጦር በየበኩሉ እየወጋ የንጉሡ ነገሥቱ ሥልጣን በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ በኩል ገና አልተደላደለም ። ከዚህም ጋር የጋሎቹ ወረራ ስለዠመረ ያዱ ገላውዴዎስ መንግሥት ከሃይማኖቱ ክርክር ጋር በችግር የተከበበ መንግሥት መሆኑን ፤ ከወገኖቹ ከነቤርሙዴዝ ተጣልቶ የርሳቸው ታማኝ አገልጋይ የሆነው የግዕዙ መጽሐፍ ማርቆስ አፍርንጋዊ የሚለው አሪያስ ዲያዝ ከጋሎቹ ጋር ፣ ስመ ጥሩው የንጉሡ ዋና የጦር አለቃ አፈጠ ድንግል ከእስላሞቹ ጋር እየተዋጉ መሞታቸውን አንብበናል ። እንደዚሁም ዋናው ስመ ጥር የጦር አለቃቸው ፋኑኤል የምሥራቁን ክፍል እንዲያስተዳድር ሥልጣን ተሰጥቶት ነበርና ብዙ ጊዜ ከእስላሞቹ ጋር እየተዋጋ ማሸነፉን የንጉሡ ዜና መዋዕል እንደዚህ ሲል ያመለክታል «ንጉሡ ገላውዴዎስ ወደ ምዕራብ (ጋፋትና አካባቢው) መዝመቱን ስለሰሙ እስላሞቹ የምሥራቁን ኢትዮጵያ ወረሩ ። በዚያን ጊዜ ፋኑ[illegible]ዋግቶ አሸነፋቸው ። ኑርና ጭፍሮቹ ከዋናው አለቃ ጋር ሲያመልጡ የቀሩት ተገደሉ ። ፋኑኤልም ምርኮውን ብዙ ፈረስና የጦር መሣሪያ ለንጉሡና ለእናታቸው ለንግሥት (ሰብለ ወንጌል) ላከ» (1) ። ከዚያ ደግሞ አልፍ ብሎ «ንጉሡ ተናዶ ለፋኑኤል ለተዋጊዎች አለቃ ወደ ሰዓዲን በር ሄዶ እስላሞቹን እንዲወጋ የሥልጣን መብት ሰጥቶት ስለነበረ እንዳዘዘው ሄዶ ተዋግቶ ከነጋሢዎቻቸው አንዱ ያለውን ንብረት ትቶ ሲሸሽ ሌላውን ነጋሢ ገደለ» ይላል (2) ። የግዕዙ ዜና መዋዕል ፋኑኤል በዚህ ጦርነት ሐረርን መውረሩን እንጂ ይዞ መቆየቱን አይገልጽም ። ሐረርንም ብዙ ጊዜ በዚህ ሥያሜ በመጥራት ፈንታ የምሥራቅ አገር ወይም የሰዓዲን በር ይለዋል ። ነገር ግን በዓረብኛ በተጻፈው በእስላሞቹ ሰነድ ውስጥ ፋኑኤልና ሐመልማል የሚባሉት የዓፄ ገላውዴዎስ የጦር አለቆች በተለያየ ጊዜ ውስጥ ሐረርን መያዛቸውን እንደዚህ ሲል ስለሚያረጋ

(1) ...... ሀቀመ ሕየንቱሁ ፋኑኤልሃ እም ዓበይተ ሐራሁ በዘሎን አህጉረ ሠርቅ ዘከመ ደዋሮ ወእዋልዲሃ .... ወበውእቱ ዓ.ም. (ዓመት) ሶበ ሰምዑ ነገደ ተንባላት ከመ ሖረ ንጉሥ ገላውዴዎስ መንገለ ምዕራብ ፀሐይ ሮጹ አህጉራተ ምሥራቃውያተ እለ ዘከርናሆን ። ወተቃተሎሙ ፋኑኤል ..... ወቀተለ ምእተ ወእምእተ ወእልቦ ዘአትረፈ እንበለ ሊቀ ሠራዊት ዘጕየ ኅሡረ ወሠራዊትኒ ውሑዳን እደው ዘከመ ኑር ወካልአኒሁ ወፈነወ ዕልገታቲሁ ኀበ ንጉሥ ወንግሥት እሙ ብዙኃ አፍራሰ ወብዙኃ ንዋየ ፀብእ ወትርሲተ ቀትል ... ጕንዘልማን ገጽ 37 - 39 ።

(2) ወበውእቱ መዋዕል ነደት ቅንዓቱ ከመ እሳት ወጸሐፈ ሎቱ መጽሐፈ መባሕት ለፋኑኤል ሊቀ ሠራዊት ፀብእ ከመ ይሁር እንተ ፍኖተ በር ሰዓዲን ወይጽብኦሙ ለእስላም እለ ሕየ ። ወገብረ በከመ አዘዞ ወሖረ ወሀብኦሙ ወቀተለ አሐደ እምከልኤቱ ነገሥታቲሆሙ ወካልኡ አምሰጠ ርሑቀ በገዲፈ ሆሎ ዘቦ ...... ገጽ 41 ።

ግቀ የዓረብኛው ሰነድና የዜና መዋዕሉ አጻጻፍ በመሠረቱ ሲስማሙ ይታያል ።
«. . . . . በሳፋር ወር በ፳፫ኛው ቀን በሂጅራ ዓመት በ፱፻፵፯ ረቡዕ ከሰዓት
በኋላ የተረገመው ፋትኢል አዘንግቶ ሐረር ገባ ። እንደዚሁም የተረገመውና ሃይማ
ኖት የሌለው ሐመልማል በ፳፩ኛው በጉማድ አል አኺር ወር ሐሙስ . . . . በሐረር
ከተማ ገብቶ በማግሥቱ ዓርብ ሐሲም በሚባለው በጌታችን መሬት ላይ ከሱልጣ
ኖች ጋር ተዋጋ ሱልጣኑም በሰማዕትነት ሞተ ። ለእርሱም እግዚአብሔር የደጉችን
ምሕረት ሰጥቶ የተመረጠው መሐመድ እንደሚፈርደው በዕረፍት ቦታ ያስቀም
ጠው . . . . . ይኸም የሆነው በሂጅራ ዓመት በ፱፻፳፮ ነው . . . . .»(1) የፋትኤ
ል ሐረርን መያዝ በሂጅራው ዓመት ሲታሰብ እንደ አው. ቀ. ፲፫ መጋቢት ፲፭፻፵፱
ዓ. ም. ሲሆን የሐመልማል ደግሞ በዘጠነኛው ዓመት በ፲፭፻፵፱ ዓ. ም. ፴፩ መጋ
ቢት እንደሚሆን ቸሩሊ ያስገነዘቡት በኛ የፋትኤል አገባብ በ፲፭፻፵፱ የሐመልማል
ደግሞ ንጉሡ በሞቱበት ዓመት በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ይሆናል ። ነገር ግን የገላውዴዎስ
ዜና መዋዕል ባለፈው እንደተመለከተው የንጋሢውን ገዳይ ፋትኤልን ሲያደርገው
ዓረብኛው ሐመልማልን አድርጎታል ። ምናልባት ሁለቱም በየበኩላቸው እንዳ
ንድ መስፍን ገድለው እንደሆነ አይታወቅም ።

አሁን ግን ከፋትኤል ጦርነት በ፲፭፻፵፱ ዓ. ም. ያመለጠው ኑር እንደገና ተዘጋ
ጅቶ መጥቶ ከዔ ገላውዴዎስ ጋር ተዋግቶ በማሸነፍ የግራኝን ደም ብቻ ሳይሆን
በቅርብ የሞተውን የሱልጣኑን ደም ሲበቀል በሰፊው እናገኘዋለን ። ኑር ከዚህ በፊት
እንዳልነው የወዚር ሙጃሂድ ልጅ ነው ። የሙጃሂድ አያቱ አብደላ አባቱ ገራድ
አሊ ሱሁ ይባላሉ ። አብድራዛቅ አህመድ ዲንና አቡን ዳዋህ የሚባሉት ወንድሞቹ
ናቸው ። ጸሐፊው ዓረብ ፋቂህ ሙጃሂድን ስመ ጥሩው ፈረሰኛ አስፈሪው አንበሳ
ይለውና ባዬ ልብነ ድንግልና በግራኝ ጦርነት ጊዜ የክርስቲያኖቹን የጦር አለቃ
እርባ ሽመልን ባንድ ጊዜ በትር ከፈረሱ ላይ ገልብጦ ከመሬት ላይ እንደጣለው ያረ
ጋገጠውን በዚያው በጦርነቱ ምዕራፍ ላይ ያነበብነው ትዝ ይለናል ።

በተረፈ ሙጃሂድ ከመዠመሪያ ከባሉ ዠምሮ በሸምብራ ኩሬ በደዋሮ በይ
ፋት በዋስል በወጅ በግራኝ አህመድ ውስጥ ጦር እየመራ በብዙ ቦታ እየተዋጋ
ብዙ ሕዝብ የፈጀ ነው ። ከአምዱሽ ጋር ሆኖ እምባ ግሺንንና በውስጡ ያለውን ሀብ
ትና የሀር ልብስ ለመበዝበዙ ታሪክ ነገሥቱ ''ወበይእቲ ወርኃ የካቲት አመጹ ተሰ
ዕረ ወተበርበረ ግሺን እምባ ነገሥት ወተረክበ በህየ ብዙኅ ልብስ ሐሪር መዛግብተ
ነገሥት . . . . . ወዘንተ ገብሩ ወዚር ሙጃሂድ ወአምዱሽ'' ያለውን እናስታውሳ
ለን ። ግራኝ ከመሞቱ ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ውስጥ ሙጃሂድ ወጅን ቀጥሎ በአ
ባስ ፈቃድ በጉምድርን ተሾሞ ያስተዳድር ነበረ (2) ።

ልጁን ኑርን ዓረብ ፋቂህ በመጽሐፉ ብዙ ጊዜ እንሥቶት አይገኝም ። ባንድ

(1) L'Islam di ieri e di oggi. E. Cerulli. ገጽ 198 - 200
(2) ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 48 ቍጥር 2 ። ታሪክ ነገሥት ገጽ 104
Etudes sur l'histoire d'Ethiopie ገጽ 17 - 18 ።

ቦታ ላይ ብቻ ፈራቃሃም ዲን ከይማም (ግራኝ) ሞት በኋላ ከኤሚር ኑር የሙጃሂድ ልጅ ጋር ወደ ሐረር ሄደ ሲል እንሥቶታል (1) ። ሙጃሂድ ኑርን የወለደው ከግራኝ አህመድ እህት መሆኑ ባንዳንድ ጽሑፍ ላይ ተመልክቶ ይገኛል (2) ። ከግራኝ ሞት በኋላ ደግሞ ኑር የዚህኑ ያጐቱን ሚስት ወደፊት ሲያገባ እንመለከታለን ።

ኑር በግራኝ አህመድ ዘመን በጦርነቱ ቦታ ከአባቱም ጋር ያለአባቱም መገኘቱ የታወቀ ነው ። ነገር ግን በጦርነቱ ዘመን ወጣት ስለሆነ መጽሐፉ አባቱን ሙጃሂድንና ሌሎቹን ሹማምንት ሲያነሣ እርሱን የማያነሣው ወጣት ስለሆነ ወይም ለመጠራት የሚያበቃ የሹመት ደረጃ በዚያን ጊዜ ስለሌለው ይሆናል ።

ግራኝ በሞተበት ጊዜ ከግራኝ ሚስት ከድል ወንበራ ጋር ሆኖ የአባቱ ግዛት ከነበረው ከበጌምድር ወደ ሐረር ሲመለስ እሙሉ ሰውነትና አዝማችም ለመሆን የደረሰ ይመስላል ። ስለዚህ ነው ዓረብ ፋቂህ ፈራቃሃም ዲን ከግራኝ ሞት በኋላ ከኤሚር ኑር ጋር ወደ ሐረርጌ ተመለሰ ያለው ። የሙጃሂድና የልጁ ነገዳቸው በዛሬ በቃል አተራረክ እነዚያ በጦርነቱ ሰዓት ከግራኝ ጋር ሆነው ብዙ ጊዜ ሲዋጉ ያነበብናቸው መሬሃን ወይም መራሂሃን ከሚባሉ ከሱማሊ ወገን ነው ። ነገር ግን የግዕዙ ሰነድ የነሙጃሂድን ነገድ ሱሐ ይልና ሰዎቹን ሱሐውያን ይላቸዋል ። ዓረብ ፋቂህም የሙጃሂድን አባት ገራድ አሊ ሱህ ስለ ሚለው ሁኔታው የተያያዘ ነው ። በዚህ ምክንያት ከግራኝ ሞት በኋላ ኑር ከሐረርጌ ተመልሶ ከወዚር አባስ ጋር መጥቶ ከዚህ በፊት ከገላውዴዎስ ጋር ከተ[illegible]በኋላ ተሸንፎ መሸሹን ታሪከ ነገሥቱ እንደዚህ ሲል ይጠቅሳል ። «ከሱሐውያን ሕዝብ ወገን የሆነውን የሙጃሂድን ልጅ ከነሀብቱ (ገላውዴዎስ) ዕሩቅ ድረስ አባረረው»(3) ።

ስለዚህ ኑር በወጅ ሳለ አባስ ተዋግቶ የሞተ ጊዜ እርሱ አምልጦ ወደ ሐረር ተመልሶ ሥልጣን ከያዘ በኋላ መዠመሪያ ከፋኑኤል ጋር ቀጥሎ ሐመልማል በመጋቢት ወር በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ለስሙ በሐረር ከተቀመጠው ሱልጣን ጋር በተዋጋበት ጊዜ ኑር የሙጃሂድ ልጅ ተዘጋጅቶ ዓፄ ገላውዴዎስን ሲወጋ መጥቷል ማለት ነው ። ዓመቱና ወሩ ሲታሰብ ሐመልማልና ስሙ ያልታወቀው ሱልጣን የተዋጉበትና ኑር ካፄ ገላውዴዎስ ጋር የተዋጉበት ጊዜ አንድ ነው ።

አባስ በሞተበት ጊዜና አሁን ኑርና ዓፄ ገላውዴዎስ ለውጊያ በሚዘጋጁበት ዓመት መካከል የአሥራ አራት ዓመት ጊዜ አለ ። ይኸንንም የምናውቀው አንደኛ ግራኝ አህመድ የሞተው በ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. መሆኑን ከዚያ ቀጥሎ ታሪከ ነገሥቱ "ወእምድኅረ ሞተ ግራኝ በ፱ ዓመት ቀተሎ ለአባስ" ሲል ስለአረጋገጠ አባስ የሞተው በ፲፭፻፵፬ ዓ. ም. በመሆኑ አሁን ደግሞ ገላውዴዎስና ኑር የተዋጉት ዓፄ ገላውዴዎስ በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት በ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ስለሆነ ነው ።

በዚህ በ፲፬ ዓመታት ውስጥ የሙጃሂድ ልጅ ኑር ከርሱ በማዕርግ ከፍ ይል የነ

(1) ዓረብ ፋቂህ ገጽ 92
(2) L'Islam di ieri e di oggi. E. Cerulli. ገጽ 156 ቍ. 61
(3) ወለኑርኒ እምሕዝበ ሱሐውያን ዕብነ ሙጃሂድ ሰደዶ ዕሩቀ እምኵሉ ሥናያቲሁ ፡ ገጽ 104 ።

ያዔ ገላውዴዎስ ትግልና የሕይወታቸው ፍጻሜ

በረው ወዚር አባስ ከሞተና በ፲፭፻፴፩ ዓ. ም. ከፋኑኤል ጋር ከተዋጋ ወዲህ በዕድ ሜም ከሙሉ ሰውነት ደርሶ ለጠቅላላው የእስላም ጦር የበላይ ኃላፊ ሆኖ ያስተዳ ድር ጀመር ማለት ነው ። በዚህም ጊዜ ከክርስቲያኖቹም ከጋሎቹም እየተከላከለ ሐረርጌ ተቀምጦ በሚያስተዳድርበት ሰዓት ከተማው ሐረር የወረራ አደጋ እንዳይ ደርስበት ዙሪያውን እስከዛሬ የሚታየውን ግንብ ማሠራቱን ፤ በመልካም አስተዳ ዳሪነቱና ይኸን ግንብ ከማሠራቱ፡ የተነሣ በእስላሞቹ ዘንድ እንደ ጻድቅ የሚቆጠር መልካም መስፍን መሆኑን በዘመኑ የነበሩ ጸሐፊዎች እና አቡበከር ኢብን መሐ መድ (አልዊ ሰንባል) ያረጋግጣሉ (1) ። በነርሱም ጽሑፍ አንዳንድ ጊዜ አሚር ወይም ጻድቁ አሚር አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አሚር አል ሙሚኒን የአማኞች መስፍን ይባላል ። ከግራኝ ሞት ወዲህ ዓፄ ገላውዴዎስን በመግደል የግራኝን ደም ስለተበ ቀለ ሳሂብ አልፋትህ አል ታኒ ሁለተኛው ድል አድራጊ ተብሏል እንደኛው ድል አድራጊ ሳሂብ አል ፋትህ አል አዋል ተብሎ የተሠየመው ግራኝ አህመድ የኢብራ ሂም ልጅ ነው ።

የኛ ታሪክ ነገሥት በበኩሉ ኑርን የግራኝ የእኅቱ ልጅ መሆኑን ከማረጋገጥ ጋር ከመዋጋት የደረሰበትን ምክንያት እንደዚህ ሲል ያስከትላል ። «ግራኝ የሞተ ለት ሚስቱ ድል ወንበራ ወደ ሀገሯ ስትሸሽ ኑር አብሮ ከርሷ ጋር ሸሽቶ አገራቸው ሐረርጌ ገቡ ። አገራቸው ከገቡ በኋላ ላግባሽ ብሎ ቢጠይቃት እኔን ማግባት ከፈቀ ድህ መጀመሪያ ሄደህ የክርስቲያኑን ንጉሥ የባሉን ደመኛ[illegible]ደል አለችው በዚህ ምክንያት ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ሊዋጋ መጣ» (2) ።

ከዚህኛው ደግሞ በተለይ ደጃች ኃይሉ እሸቴ ሰብስበው ያደራጁት ታሪክ ነገ ሥት በፓሪስ ፻፵፭ ቁጥር ተሰጥቶት የተቀመጠውና ብዙ ጊዜ ለዚህ መጽሐፍ መሠ ረት አድርገን የምንጠቅሰው ከዚህ ሰፋ አድርጎ ጉዳዩን በማከታተል በግዕዝ የተረ ከውን ትርጉሙን በአማርኛ እንመልከት »በ፸፻፶፪ ዓመተ ዓለም (3) በንገሡ በ፲፬ኛው ዓመት በመጋቢት ፫ ቀን እሑድ የሙጃሂድ ልጅ ኑር ፲፭፻ ፈረሰኛ ፰፻ ነፍጠኛ ፤ ቀስተኛውና ሰይፈኛው ቁጥር ስፍር የሌለው ተዋጊ ወታደር ይዞ ወደ ፈጠጋር መምጣቱን ወሬ ነጋሪዎች ነገሩዋቸው ። ...... ከንጉሡ ጋር የነበ ረው ጦር ፻፺፰ ፈረሰኛ ፺፻ እግረኛ ፤ በነፍጥ የሚዋጉ ፩፻ ፤ በቀስት የሚዋጉ ፰፻ ናቸው ...... የነኛን የጦር ብዛት ያዩ ጦር እስኪሰበሰብ ድረስ ከኑር ጋር ጦርነት እንዳይገጥሙ ቢመክሯቸው ..... አስቀድሞ ባለቤቱን ሳያስር ኃይለኛ ባንዱ ቤት ገብቶ ንብረቱን ሊበዘብዝ አይችልም (4) እኔም በዚች መሬት በሕይወት እስ

(1) ዓረብ ፋቂህ በረኔ ባሴት ትርጉም ገጽ 48 ቁጥር L'Islam di ieri e di oggi. ገጽ 168 ቊ. 125

(2) ረኔ ባሴት ያሳተመው ታሪክ ነገሥት ገጽ 21 - 13 ። በዚህ ጋብቻ ኑር ገላውዴዎስን ስለገደለ በአ ማርኛ አነጋገር «እሺ. ኑር ብላ ነው ያስገደለችው» የሚል ተጽፏል ።

(3) ፸፻፶፪ ዓመተ ዓለም የሚባለው ከ፸፻፶፪ ላይ ቢቀነስ ገላውዴዎስ የሞቱበት ፲፭፻፶፪ ዓ.ም. መገ ኘቱን አንባቢ ያስተውል ። እዚህ ላይ የሞተበት ዓመት ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. በመሆን ፈንታ ፩ ዓመት ታክሏል ።

(4) ማቴ. ምዕ. 12 ቁጥር 19

ካለሁ ድረስ የአገሬን ጥፋት ማየት አልችልም ብለው ወደ ጦርነቱ ተጓዙ . . . . .» ይልና ከዚያ እልፍ ብሎ ደግሞ ዓፄ ገላውዴዎስ ኑር ወደሠፈረበት ሄደው ያንድ ደንጊያ ውርወራ ርቀት ባለው ሥፍራ ፊት ለፊት በሠፈሩበት ሰዓት የጠላትን ጦር ብዛት ዓይተው አለመደንገጣቸው ባጠገባቸው ከቆመው አንዱ በነቢያት ዘመን የሆነውን ተርኮ ሕዝብ ማስጨረስ እንዳይሆን የሸሸት ምክር ቢያመጣ ፊታቸውን በቁጣ ወደ ሰውዬው አዙረው «እረኛ ነፍሱን ለማዳን ሲል በጎቹን ትቶ ይሸሻልን? እረኛ (መልካም እረኛ) ስለበጎቹ ሕይወቱን ይሰዋል ምንደኛ የተቀጠረ ግን ነፍሱን ለማዳን ሲሸሽ ስለበጎቹ አያዝንም ። እኔ እንደምን አድርጌ እሸሻለሁ? እንዴትስ አድርጌ ባሌ ሞተብኝ ብላ የምታለቅሰውን ሴት አባቴ ሞተብኝ ብሎ የሚያለቅሰውን ልጅ ወንድሜ ሞተ ብሎ የሚያለቅሰውን ወንድም እያለሁ? ።

ስለዚህ እኔ ስለክርስቶስና በበታቹ ስለሚተዳደረው መንጋዬ (1) መሞትን እመርጣለሁ ፤ እኔም ሞቼ በጎቹ ቢበተኑ የዕረኞች ጌታ (2) ከኔ ላይ አይፈላለግም ፈርቼ ቢበተኑ ግን ይጠይቀኛል . . . . .» ብለው በቁጣ እንደመለሱት ያረጋግጣል (3) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ እንሽሽ ብሎ ለመከራቸው ሰውዬ የሰጡት ይህ መልስ የጉብዝና የቆራጥ መልስ መሆኑን ስለ ሕዝባቸው ስለወገናቸው ፍቅር ለመሠዋት የተዘጋጁ መሆናቸውን ከመመልከታችን በላይ የሚሰጡት መልስ ክርስቶስ በወንጌል ስለ መልካም ዕረኛና ስለመጥፎ [illegible]ደኛ እረኛ በወንጌል የተናገረውን መሠረት አድርገው ስለሆነ በነእንድርያስ አቪዬዶ የሃይማኖት ክርክር ጊዜ ያሳዩትን የሊቅነት መልስ አሁንም በዚህ ሕይወታቸው አደጋ ላይ ባለበት ጊዜ መካከል ለሞታቸው አዝኖ ሽሽትን ለሚመክራቸው በሚሰጡት መልስ ጉብዝናቸውን ብቻ ሳይሆን ሊቅነታቸውንም ያሳያሉ ።

እውነት ነው አንዳንድ ዜና መዋዕል አዘጋጅዎች ንጉሣቸው ያላለውን እንዳለ እያስመሰሉ እነርሱ ራሳቸው ከብሉይና ከሐዲስ እየጠቀሱ አሰማምረው በንጉሣቸው ስም የሚጽፉ ሞልተዋል ። ነገር ግን በወጣትነታቸው ጊዜ ዓጼ ገላውዴዎስን አባትዬው ከወንድሞቻቸው ለይተው መንፈሳዊ መጽሐፍ እስኪበቃቸው ድረስ አስተማሩዋቸው ያለውን ስናስታውስ እላይ እንዳልነው ከነጎንዛሌስ ከነእንድርያስ አቪዬዶ ጋር የሃይማኖት ክርክር በተደረገ ጊዜ ንጉሡ በሚያመጡት ጥቅስና ክርክር እንቸገር ነበር ብለው ፈረንጆቹ ራሳቸው የጠቀሱትን ስናስብ ይኸ ቃል ከርሳቸው እንደበት በቀጥታ አልወጣም ብለን ለመጠራጠር አንችልም ። በአንደበታቸው የወረወሩትን ቃል ወዲያው ተዋግተው ሕይወታቸውን ለሕዝባቸው አሳልፈው በመስጠትና በመሞት በተግባር አረጋግጠዋል ።

ምናልባት ሊያጠራጥር የሚችለው የጦር ሠራዊቱ ቍጥር ነው ። ጸሐፊው

(1) ሕዝቤ ማለት ነው
(2) እግዚአብሔር ለማለት ነው
(3) ታሪክ ነገሥት ገጽ 114 ። ዮሐንስ ምዕ. 1 ቍጥር 11 - 16

የንጉሡን ልበ ሙሉነት ለማመልከት ሲል የጠላታቸውን የኤሚር ኑርን የጦር ሠራ ዊት ሲያበረክት የርሳቸውን በጣም ያሳነሰው ይመስላል ። ይኸን የመሰለውም እጸ ጸፍ በቀድሞ ጸሐፊዎች ዘንድ እየተደጋገመ ብዙ ጊዜ ትንሽ ወታደር ይዞ በብርቱ ጊዜ ብቻውን ንጉሡ ጠላቶቹን ተዋግቶ መለሰ የሚል ይገኛል ።

በ፲፭ኛው መቶ ዓመት ከክርስትና በፊት የነበረው ዳግማዊ ራምሲስ የግብፅ ንጉሥ የመካከለኛው ሕዝብ (ኬታ ሂቲቲ) ሽፍቶበት ሊዋጋ በሄደ ጊዜ ጭፍሮቹ ትተውት ሸሽተው ብቻውን በጠላቶቹ ፊት ስለተገኘ «ቀስተኞቹ ፤ ፈረሰኞቼ ትተ ውኝ ሸሹ . . . . . አባቴ አሞን ሆይ . . . . ባልታወቁ ሕዝቦች መካከል . . . . . . ብቻዬን ነኝ . . . . . . ፈረሰኞቼን እርዱኝ ብዬ ስጮህ ትተውኝ ሸሹ ነገር ግን ከሺ ቀስተኛ ፤ ከሺ ፈረሰኛ አንተን እመርጣለሁ» ብሎ ለአምላኩ ለአሞን ቢጸልይ «ራምሲስ ሆይ ድምፅህን ሰማሁ አጠገብህ ነው ያለሁት ከንዴ ካንተ ጋር ነው ...» ብሎ ከመለሰለት በኋላ ብቻውን የተቀመጠበትን መንኩራኩር እስነሥቶ ከጠላ ቶቹ መካከል ገብቶ በመበታተን እንዳሸነፋቸው ተጽፏል (1) ።

እንደዚሁም በኢትዮጵያ ባፄ ዓምደ ጽዮን ላይ የአዳሉ ንጉሥና የወላስማው ተወላጅ ሰበርዲን ተነሥተውበት ሊዋጋ በሄደ ጊዜ ሠራዊቱ በሌለበትና እርሱም ታሞ በሰነበተበት ሰዓት ጥቂት ወታደሮች ይዞ ተዋግቶ እንዳሸነፈ የጦርነት ታሪኩ ይገልጽለታል (2) ።

ይኸ ሁሉ ብቻውን ወይም ትንሽ ጦር ይዞ ብዙውን ሠራዊት አሸነፈ ብሎ ለማድነቅና በሰሚ ዘንድ ለማስደነቅ ሲባል ነው ። ይሁን እንጂ የዓፄ ገላውዴዎስ ከነዚህ ለየት ይላል ። ሠራዊታቸውም በግራኝ ወረራ የፈራረሰውን አውራጃ መልሶ ለማቅናት በያለበት ተበታትኗል ። ደግሞም ይኸንኑ እነሥተኛ ጦር ይዘው በመዋጋታቸው ሞቱ እንጂ እርሳቸው አላሸነፋም ። አሁን የጦርነቱን ሁኔታና የሚያሳዝነውን አሟሟታቸውን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፻፶፪

## ባፄ ገላውዴዎስና በአሚር ኑር መካከል የተደረገው ጦርነት — ያፄ ገላውዴዎስ ሞት (፲፭፻፶፩ ዓ. ም. መጋቢት ፳፯ ቀን) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ኑር ብዙ ጦር ይዞ መጥቶ ፈጠጋርን መውረሩን የሰሙት መጋቢት ፫ ቀን እሑድ የሁዳዴ ጾም በገባ በአራተኛው ሳምንት መሆኑን ታሪክ ነገሥቱ ያረ ጋግጣል ። አሁን ግን ጦርነቱን የገጠሙበትን ቀን ይኸው ታሪክ ነገሥት በኢትዮ

(1) የኢት. ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዌ እስከ ይኩኖ አምላክ ምዕ. 8
(2) ያምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ ፔሩሾ ያሳተመው ገጽ 381 - 390 ። የኢት. ታሪክ ካፄ ይኩኖ አም ላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ምዕ. 14 ገጽ 72 - 89

ጵያ በሰባተኛው ወር (1) በሮማውያን በሦስተኛው (2) የሁዳዴ ጾም በገባ በስምን ተኛው ሳምንት በመጋቢት ፳፯ ቀን ሐሙስ በስድስት ሰዓት ላይ መሆኑን ያመለክ ታል (3) ። በዚህ ዓይነት ወሬውን በመጋቢት ፫ ቀን ሰምተው በመጋቢት ፳፯ ቀን ተዋግተዋል ማለት ነው ።

ስለዚህ የኑርን መምጣት በሰሙበትና ጦርነቱን በገጠሙበት ጊዜ መካከል የሐያ አራት ቀን ጊዜ አለ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱ ከያለበት ጦራቸውን ሳያሰበስቡ በዚያ ታሪክ ነገሥቱ በጠቀሳቸው ቍጥራቸው ባነሰ ጦር ኑርን ገጠሙት ለማለት ይቸግራል ። ነገር ግን ጦሩ ግማሹ በስሜን ግንባር ስለሆነ ከሩቅ ሥፍራ ለመሰብሰብ የ፳፬ቱም ቀን ጊዜ አጭር መሆኑ የታወቀ ነው ። መቼም ለጦርነት ድል መፍትሔው የመሣሪያ ጥራት የጦርነት ዘዴና ስልት ድፍረትና ዝግጁነት እንጂ የተዋጊና የሰው ብዛት እምብዛም መሆኑ ዓፄ ልብነ ድንግልና በግራኝ አህ መድ መካከል በተደረገው በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. በሽምብራ ኩሬ ጦርነት ታውቋል ። በዛሬም ዘመን በዓረቦችና በእሥራኤሎች በቪዬትናም ጦርነት የሚታይ ነው ። ስለ ዚህ በዚህ ዓፄ ገላውዴዎስ ዘመን ደግሞ ከዘዴውና ከድፍረቱ ጋር ድል የሚገኘው በጦርና በሰይፍ በቀስት በትር ብቻ ሳይሆን በተተኳሽ ጠበንጃና ጥይት ነው ። በሰ ልፍ ውስጥ በርከት ያለ ጠበንጃ ያለው ወገን ጠላቱን ለማሸነፍ የበለጠ ዕድል አለው ።

ታሪክ ነገሥቱ በኑር ጦር ሠራዊት ውስጥ ፳፻ ባለጠበንጃ ዓፄ ገላውዴዎስ በኩል ግን ፩፻ ብቻ መኖራቸውን አስተካክሎ ገልጿል ። ይኸውም እውነት ሊሆን ይችላል ። ዓፄ ገላውዴዎስ በኩል ያሉት ፩፻ ባለጠበንጃዎች የሚላቸው እነዚያ ከግራኝ አህመድና ከጋላ ጦርነት የተረፉትና ወዳገራቸው ያልሄዱት የፖርቱጋል ተወላጆች ናቸው ። ከነዚህ በቀር በምጥዋም በሌላም ወደብ ከፖርቱጋልም ከሕን ድም ሌላ ተጨማሪ ርዳታ እንዳልመጣ ግልጽ ነው ።

ለአሚር ኑር ግን ከዘንተራ ጦርነት ወዲህ ከግራኝ ባለቤት ጋር ወደ ሐረር የተ መለሱት አርባ ቱርኮች የቀሩት ቍጥራቸው የማይታወቅ የሕንድና የዓረብ የፋርስ የቅጥር ወታደሮች ከነዚህም በቀር በ፲፱ ዓመታት ውስጥ አሚር ኑር ከያለበት እየተ ላላከ ያስመጣቸው ባለ ጠበንጃዎች ታሪክ ነገሥቱ እንዳለው ቍጥራቸው ፳፻ ስለ ሚሆን በሁለቱ ባላጋራዎች መካከል ያለው የጦር ኃይል ልዩነት በጣም የተራራቀ መሆኑን ስንመለከት በዚህ ጦርነት የኑር አሸናፊነትና ዓፄ ገላውዴዎስ መሸነፍ አስገራሚ ሊሆን አይችልም ።

የሁለቱ ወገን ጦር ተሰልፎ ፊት ለፊት በሚተያዩበት ጊዜ ታሪክ ነገሥቱ የተ ክለ ሃይማኖትን መልክ የደረሱት እጨጌ አባ ዮሐንስና አባ መቃርስ የሚባሉ ከሌ

(1) እንደ ኢትዮጵያ ቍጥር ከመስከረም እስከ መጋቢት ፯ ወር ይሆናል ።
(2) እንደ አው. አቈጣጠር ልማድ የወር መጀመሪያ ጥር ሲሆን መጋቢት ፫ኛ ወር ነው ።
(3) እመ ፳ወ፯ ለመጋቢት ሳብእ ወርኀ እምአውራኂነ ግልሰ ወርኀ እም አውራኀ ሥርዓቶሙ ለሮም . . . . . . ወ፰ቱ ሰንበተ ጾም በዕለተ ሐሙስ ዘጸሎት ጊዜ ፮ቱ ሰዓት መዓልት ኮነ ቀትል ማዕ ከለ ንጉሥ ገላውዴዎስ ወማዕከለ ኑር . . . . . . ታሪክ ነገሥት ገጽ 115 ።

ገላውዴዎስ መጥተው "ከሰማይ መንግሥትና ከም
ሎች መነኮሳት ጋር ወደ ዓፄ ገላውዴዎስ መጥተው "ከሰማይ መንግሥትና ከም
ድር መንግሥት ምረጥ ። ዛሬ ሳትዋጋ ከደርክ ታሸንፋለህ ፤ ሳታድር ከተዋጋህ
ትሞታለህ ፤ ነገር ግን መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ....." እንዳሉዋቸውና ዓፄ
ገላውዴዎስ «ስለመንግሥተ ሰማያት መሞት ይሻለኛል» ብለው እንደመረጡና
ጦርነቱን እንደገጠሙ ይገልጻል (1) ።

ይኸን የመሰለው የመነኮሳት ጥያቄና የነገሥታት መልስ እንደዚያው የተዋ
ጊን ወታደር ቍጥር እንደማሳነሱ ብዙ ጊዜ በተለይ በዚህ ዘመን በተዘጋጀው ዜና
መዋዕል ላይ በርከቶ ይገኛል ። በቅርቡ እንኳን ባዔ ዮሐንስና ባዔ ምኒልክ መካ
ከል በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. መሳለፍ በተደረገ ጊዜ አንድ ባሕታዊ ከጫካ ወጥቶ «ወደ
ሸዋ ሄደህ የተዋጋህ እንደሆነ ታሸንፋለህ ነገር ግን ትኰነናለህ ። ነገር ግን ወደ
ሱዳን ሄደህ የተዋጋህ እንደሆነ ግን ትሞታለህ ግን መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ»
ስላላቸው ሱዳን ዘምተው መተማ ሞቱ እየተባለ ይወራል ።

ዳሩ ግን ዓፄ ገላውዴዎስ እንደውነቱ ዕለቱን ተዋግተው ቢሞቱ የሚጸድቁ
በት ውለው አድረው ጦር አደርጅተው ቢዋጉና ቢያሸንፉ የሚኰነኑበት ምን የበቃ
ምክንያት አለ ? ። ጠላትን ማሸነፍ ማስኰነኑ በጠላት ተሸንፎ መሞት ማጽደቁ
ከምን ሕጋዊ ትእዛዝ ላይ ሊገኝ ይችላል ። ከጠላቶቻቸው ጋር ዕለቱን ተዋግተው
ሳይሞቱ ተዘጋጅተው ውለው አድረው የተዋጉትና ጠላቶቻቸውን ያሸነፉት መሪ
ዎችና ነገሥታትስ ተኰንነዋል ማለትስ ይቻላልን ? ። ስለዚህ ታሪክ ነገሥቱ የሚ
ለው እውነት ከሆነ በሚያሳዝን አኳኋን በጥይት ተመትተው በብዙ ጦር ተወግ
ተው ለሞቱት ንጉሥ ኃላፊዎቹ መነኰሳቱና ንጉሡ ራሳቸው ናቸው ማለት ነው ።

ከዚህ እያይዞ አሁንም ታሪክ ነገሥቱ ይህ ጊዜ መጋቢት ፳፮ ቀን ስለሆነና
ፋሲካ ስለተቃረበ መኳንንቱ ወደ ንጉሡ ቀርበው «ኢባክዎ ፋሲካን በመብልና
በመጠጥ አብረን በደስታ ከዋልን በኋላ ከዚያ ወዲያ ይዋጉ» ብለው ቢለምኗቸው
«በልቼ ጠጥቼ መብሉም መጠጡም የሚወድቀውን ይህን ምድራዊ ፋሲካ አላየ
ውም ። ነገር ግን መብሉና መጠጡ ወደማይወድቅበት ሄጄ በሰማይ ፋሲካን ከጌ
ታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እውላለሁ« ብለው እምቢ ብለው እንደመለሱ ፤ ፪ኛ
ንጉሡ ነገሥቱ ከመልኳ ማማር የተነሣ ወደዋት ከቄሱ ከባሏ ቀምተው ያስቀመ
ጧት ዕቁባት እንደ ነበረቻቸው እርሷም በዚሁ ጊዜ «ስለ ፍቅሬ ስትል አትሙት
ብኝ» ብላ ብትለምናቸው «ለማን ስል የምሞት ይመስልሻል ባንቺ ምክንያት እይ
ደለምን አንቺን የቄሱን ሚስት በኃይል ቀምቼ የወሰድሁበትን ኃጢአቴን ከደሜ
በቀር የሚያነጻው የለም» ብለው እንደመለሱላት ይገልጻል ።

ይኸን ሁሉ ከተናገሩ በኋላ ጦርነቱን እንደገጠሙ ይገልጽና ውጊያው ሦስት

(1) ወሖረ ይዳባእ ምስለ ኑር እንዘ ይትረዓዩ ገጸ በገጽ መጽኡ ኀበ ንጉሥ ገላውዴዎስ አባ ዮሐንስ መምህረ ደብረ ሊባኖስ ዘደረሰ መልክአ እቡነ ተክለ ሃይማኖት ወአባ መቃርስ ....... ያቤ ልዎ ለንጉሥ "ኅረይ እመንግሥተ ሰማይ ወእመንግሥተ ምድር እመሰ ኃደርከ ትመውእ ወለ እመ ኢሀደርከ ይእዜ ትመውት ወትበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማይ ....." በቤ. መጻ. የሚገኝ ታሪክ ነገሥት ገጽ 36 ።

ቀን እንደቆየ በዚህም ጊዜ በተለይ በሦስተኛው ቀን ውጊያው ከፋኛ ጸንቶ ወፍራም ደመና ሰማይን እንደሸፈነው የተነሱም ጢስ ፀሐይዋን እንደጋረዳት ብዙም ሰው እንደተላለቀ በዚህም በሦስተኛው ቀን ጽኑ ጦርነት ንጉሡ ፊታቸውን ሳይመልሱ በርትተው ሲዋጉ በአንዲት ጥይት እንደተመቱና እንደ ቆሰሉ ውጊያውን ሲቀጥሉ በዚሁ ጊዜ ሃያ የእስላም ፈረሰኞች እንደከበቧቸውና በጦር ወግተው እንደ ስመ ሞክሼያቸው እንደ እንጾኪያው ተወላጅ (እንደ ገላውዴዎስ) እንደገደሏቸው ያመለክትና ከዚያ እነዚሁ ባላጋራዎቻቸው ጭንቅላታቸውን ቆርጠው ወስደው ለመስፍናቸው ለአሚር ኑር እንደ አሳዩትና እሱም ተደስቶ የተቆረጠ ጭንቅላታቸውን በአህያ አስጭኖ ወደ አገሩ እንደተመለሰ ያረጋግጣል (1) ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ነገሥታት አገራቸውን እያገለገሉ ፍጻሜያቸው አሳዛኝ የሆነ ሞልተዋል ። ዓፄ እስክንድር በአርጎ ሰዎች (ዋጅራትና ደንከል) ተክላይ የሚባል ሹማቸው ስለተገደለ የርሱን ደም እበቀላለሁ ብለው ሲዋጉ በቀስት ፍላጻ ተመትተው ሞተዋል ። ዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ኢትዮጵያን በመልካም አስተዳድረው ባረጁበት ጊዜ ሚስታቸው እቴጌ መለኮታዊትና ልጃቸው ተክለ ሃይማኖት አድመው ሸሽተው ከተቀመጡበትና ከተኙበት አልጋ ላይ እንዳሉ ጳውሎስና ዳርመን የሚባሉ የሚስታቸው ወንድሞች በጥይት አስመትተው አስገደሏቸው ። ዓፄ ዮሐንስ ፬ኛ በጐንደር የፈሰሰውን የሕዝባቸውን ደም ለመበቀል ሱዳን ዘምተው ሞተው በሚ[illegible]ን አኳኋን ጭንቅላታቸው እንደተቆረጠ እናስታውሳለን ።

ነገር ግን ከማናቸውም ነገሥታት ያፄ ገላውዴዎስ ያገዛዛቸውና ያሟሟታቸው ሁኔታ በጣም አሳዛኝ ነው ። በወጣትነት ዕድሜ የወደቀ መንግሥት ከሟች አባታቸው ወርሰው ግራኝን ለመጣል ያደረጉት ትግል ፤ ግራኝ ከመውደቁ በፊት ዮሐንስ ቤርሙዴዝ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊክ ትሁን አለዚያ ይገፉ የመጣሁዋቸውን የድል በር የከፈቱትን የፖርቱጋል ወታደሮች ይገፉ ወደ አገሬ እመለሳለሁ በሚልበት ጊዜ ፥ ግራኝ ከሞተ በኋላ እንድርያስ ኦቪዬዶና ተከታዮቹ በታላቅ ዝግጅት መጥተው የሃይማኖቱን ጉዳይ ከፖለቲካው ጋር እያቀራኙ ንጉሡ ነገሥቱ የነርሱን አሳብ እንዲቀበሉ ሲያስቸግሩዋቸው በሌላ ወገን ደግሞ እናታቸውና ወገኖቻቸው እነ አባ ዝክሬ አትቀበል እምቢ በል እያሉ ሲያውኩዋቸው በሁለቱ መካከል የኘህን ንጉሥ ችግር ለመረዳት ቀላል ነው ። በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ የጠፋ አገር ሲያቀኑ የተቃጠለ ቤተ ክርስቲያንና ገዳም ሲያሠሩ በደቡብ ጋሎች ደዋሮን አጠፉ ፤ ባሌን ወረሩ ፤ ወዚር አባስ ወደ ፈጠጋር ጦር ይዞ መጣ ሲሏቸው ወደ ደቡብ ሲዘምቱ ቱርኮች ምጥዋን ያዙ ከምጥዋ አልፈው አማሴንን ወረሩ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ከድቶ ለነርሱ ገባ ሲሏቸው በዚህ ጊዜ ሁሉ ያለ ድካም ያለ

(1) ወበዋንተ ፀብእ ወድቀ ርእስ ውዑይ ውስተ ሥጋ እምሥጋሁ ወዝኒ ኢክልአ እምተቃትሎ ወኢሜጠ እምተፃብኦ እስከ ሀንትዎ መጠነ እስራ ሰብአ እፍራስ ወረገዝዎ ገቦሁ በኵናት . . . . ወእምዝ መተሩ ርእሶ ክብርተ ወአብኡ ለመስፍኖሙ . . . . . ጉንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕላቸው ምዕ. 86 ገጽ 99 - 102 ።

መስለቸት መውጣት መውረድ መውጋት ማዋጋት የርሳቸው ፈንታ ነው ። እሁ
ንም የኑርን ፈጠጋርን መውረር የሰሙት በጉጃም የደብረ ወርቅን ቤተ ክርስቲያን
ራሳቸው ቆመው ሲያሠሩ መሆኑን ዠምስ ብሩስ ያረጋግጣል (1) ።

ስለዚህ የመዠመሪያውን የግራኝን ተከታይ ወዚር አባስን ከገደሉ በኋላ እነሆ
እሁን ደግሞ ከሁለተኛው ተከታይ ከኢሚር ኑር ጋር ተዋግተው በሚያሳዝን አኳ
ኋን ሞተው ጭንቅላታቸውን ከመቈረጥ ሲደርሱ እንመለከታለን ። በዚህ ምክን
ያት ከነገሡበት ከ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ዠምሮ እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ ባለው የ፲፱
ዓመት ዘመነ መንግሥት ውስጥ ያሳለፉት ዘመን የዙረት የትግል የውጊያ ጊዜ ስለ
ሆነ ከዕረፍታቸው ጊዜ የትግላቸው ጊዜ በጣም ይበልጣል ማለት ነው ። ከመንገሣ
ቸውም በፊት የነበረው የወጣትነት ጊዜያቸው በግራኝ ወረራና አባራሪነት የተነሣ
ከአሁን የባሰ የኀዘንና የስደት ጊዜ ስለነበረ እንደ ዕድል ጠቅላላ ዕድሜያቸውን
ያለ ሰላምና ያለ ዕረፍት ስላሳለፉ የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ሕዝብ የኾሀን ንጉሥ
ውለታ ምንም ጊዜ መርሣት የለበትም ። የተቆረጠ ጭንቅላታቸው በተሰቀለበት
በሐረር ከተማ አደባባዮች ባንደኛው ላይ ሐውልት ቢሠራላቸው የተገባ ነው ።

የቢቃ ጦር በእጠገባቸው ሳይኖር በመግጠም ፈንታ ጦር ሰብስበው ገጥመ
ውት ቢሆን ኖሮ ምናልባት ሊያሸንፉ በቻሉ ብለን ከዚህ በፊት አሳብ ሰንዠረናል ።
ነገር ግን በዚህ ጊዜ በጠቃደር የሚደፈነው ቀዳዳ በየወሰኑ በየአውራጃው ብዙ ስለ
ሆነ በግራኝ ጊዜ የተበታተነውን አገር ለማቅናት ፤ በሰሜን አገር እየወረሩ ያስቸግ
ሩትን ቱርኮች ለመጠባበቅ ወታደራቸው በያለበት ስለተበታተነ መሰብሰቡ ችግር
ነው ። ወደኋላም የቀረና የተበተነው እስኪሰበሰብ ብዙ ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ ፤
እስኪሰበሰብላቸው ድረስም ወደኋላ ማፈግፈግ ተወረረ ተዘረፈ ወደተባለው እው
ራጃ ወደ ፈጠጋር ሳይሄዱና ሳይመከቱ መቅረቱ እንደ ገላውዴዎስ ላለ አገሩንና
ወገኑን አፍቃሪ የማይቻል ነው ማለት ነው ። ጦር እስኪሰበሰብ ድረስ አትግጠም
ብለው ለመከሩዋቸው «በዚች ምድር በሕይወት እያለሁ ያገሬቱን ጥፋት ማየት
አልችልም» ብለው ሲመልሱ ባሕርያቸውን አገርና ወገን አፍቃሪነት በጥልቅ ተዋ
ሕዶታል ማለት ነው (1) ።

መኳንንቱ የፋሲካን መቃረብ ምክንያት ሰጥተው ወደኋላ ለመሸሽ በመከሩዋ
ቸው ጊዜ«እግዚአብሔር ይኸን ሕዝብ እጠብቅ ዘንድ እረኛነቱን ሰጥቶኛል ። ኑርና
ጦሩ ሕዝቤን እየወረረ ከፈጀው በኋላ ባሌ ሞተብኝ ብላ ሚቱ ስታለቅስ አባቴ ተገ
ደለ ብሎ ልጁ ሲያለቅስ በሕይወቴ እያለሁ አልመለከትም» ማለታቸው ከፍ ያለ
የወገን ጥበቃ ኃላፊነት የሚሰማቸው አገራቸውን ወዳድ ወገናቸውን አፍቃሪ አም
ላካቸውን ፈሪ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸው በግልጽ ይታያል ።

የሆነ ሆኖ እግዚአብሔር ያዼ ገላውዴዎስ መሸነፍና መሞት የእስላሞቹን

(1) ጀምስ ብሩስ 2 ኛ ሊም ገጽ 217 - 219
(2) አንስ ኢይፈቅድ እርእይ ሙስናሁ ለሀገር እምጣነ ሀሎኩ በዛቲ ሕይወት ምድራዊት . . . . . ጉን
ዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕል 97

ደስታ ፍጹም እንዳያደርገው አሚር ኑር ደግሞ በበኩሉ ከዚህ ድል በኋላ ከፈጠጋር ወደ ሐረርጌ ሲመለስ ከረሃብና ከበሽታ ጋር ሠራዊቱን ጋሎች አዘሎ አቅራ ቢያ ጠብቀው ተዋግተው ብዙ ሰው እንደፈጁበት በዚህም ኑር በወጅ የፈጀውን የክርስቲያን ደም እግዚአብሔር እንዳስከፈለው የጋላን ታሪክ የጻፉት አባ ባሕርይ በዘጠነኛው ክፍል ጠቅሰውት ይገኛል (1) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ የደቡቡን አውራጃዎች ከግራኝ ይዞታ ለማስለቀቅ ጋሎች ንም እስላሞችንም እየተጠባበቁ ለመመከት በወጅ ከትመው ቤተ መንግሥት አሠ ርተው መቀመጣቸውን ከዚህ በፊት ጽፈናል ። ምናልባት ዓፄ ገላውዴዎስና ኑር በፈጠጋር ግባት ተዋግተው ንጉሡ ሞተው ሠራዊታቸው ሲፈርስ አሸናፊው ኑር ከፈጠጋር ወደ ወጅ መጥቶ ከተማውንና ቤተ መንግሥቱን ሲዘርፍ በዚያ የነበሩ ትን የተከላከሉትንም ያልተከላከሉትንም ክርስቲያኖች ፈጅቶ ይሆናል ። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ጸሐፊው አባ ባሕርይ በወጅ ያፈሰሰውን የክርስቲያ ኖች ደም አዘሎ አቅራቢያ ጋሎች አስከፈሉት ለማለት የደረሱት ወይም የኑር አባት ሙጃሂድ በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. የዚህኑ የወጅን አገር ሊያስገብር መጥቶ ከዓፄ ልብነ ድንግል የተሾመውን እስላም ደሀርንና የተከላከለ ውን ሁሉ ስለፈጀ የነዚያን ደም ጋሎች ተበቀሉላቸው ለማለት ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ኑር ከዚህም ካሁኑ ጦርነት ከጋሎቹም ውጊያ አልፎ ሐረር ገብቶ የግራኝን ደም ባፄ ገላውዴዎስ ሞ[illegible]ቅሎ ከድል ወንበራ ጋር የደስታ ኑሮ እንደ ዠመሩ ወዲያው በአገር ላይ ታላቅ ረሃብና በሽታ ተነሥቶ ሰው ከሰው ጋር መበላ ላት ስለዠመረ ከዚህ ድል በኋላ አሚር ኑርና ድል ወበንራም ምንም ያህል የደስታ ጊዜ አልገጠማቸውም ። ሁኔታውን በሚቀጥለው እናነባለን ።

ዓፄ ገላውዴዎስ የተዋጉበትንና የሞቱበትን ዓመት የግዕዙ ጽሑፍ ባንድ ቦታ ፯ሺ፶፱ ዓመተ ዓለም (፲፭፻፶፱ ዓ. ም.) ይልና በሌላ ቦታ ላይ የተዋጉትና የሞቱት በነገሡ በ፲፱ነኛው ዓመት ስለሚል የነገሡት በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. ሲሆን የሞቱበት ዓመት ፲፭፻፶፩ ዓ. ም. ይሆናል ። ይኸም ከዓረቦቹና ከፖርቱጋሎቹ አጻጻፍ ጋር ስለሚዛመድ በዚሁ ማቆም ይበልጥ የታመነ ነው (2) ።

(1) Historia gentis galla-guidi reimpression anastatique. ገጽ 225 ክፍል 9
(2) ጕንዘልማን ያሳተመው ዜና መዋዕላቸው በትርጉሙ ገጽ 175 ። L'Islam di ieri e di oggi. ገጽ 156 ።

ምዕራፍ ፲፶፫ ·
በጦርነቱ ላይ የሞቱት ያፄ ገላውዴዎስ ጭንቅላት ሐረር ሄዶ መሰቀል — በሐረር
የተነሣው ታላቅ ረሃብ (፲፭፻፶፩ - ፶፫ ዓ. ም. — የደራሲው ኀዘን ።

ታሪክ ነገሥቱን የደረሰው ሊቅ በግዕዝኛው «እንደወፍራም ደመና የጠቡ (የተ
ሸሉ) ጭስ ፀሐይዋን እስኪሸፍናት ድረስ በዚህ ቀን ጦርነቱ በረታ» ብሎ በአጭሩ
በጠቀሰው ታላቅ ጦርነት እላይ ከተመለከተው በቀር ሌላ ዝርዝር ሐተታ አልጨ
መረበትም (1) ። የዚህ የገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ደራሲ ትንሽ ሰፋ በማድረግ የኢ
ትዮጵያን ወርና የአውሮፓን ወር እያገናዘበ ዕለቱንና ሰዓቱን በትክክል እየለየ
በመጻፍ ከአለፉት ሁሉ ታሪከ ነገሥት ጸሐፊዎች የተሻለ ቢሆንም ያፄ ዓምደ ጽዮ
ንን የጦርነት ታሪክ እንደጻፈው አይሆንም ። ዓረብ ፋቂህና ካስታንሆዞ እንደዘረዘ
ሩት ዓይነት ከወዲህም ከወዲያም የሰልፉን ዓይነትና የውጊያውን ቦታ በውጊያው
ላይ ማን ማን እንደሞተ ማን እንደቆሰለ እነማን ከጦርነቱ ተርፈው እንደተመለሱ
አልገለጸልንም ። ይሁን እንጂ በዚህ ጦርነት ከንጉሡ ጋር የሞቱትን ታላላቅ የቤተ
ክህነት ባለሥልጣኖች ብቻ ከዚህ እንደሚከተለው አመልክቷል ።

፩. አባ ዮሐንስ መምህር ዘደብረ ሊባኖስ
፪. አባ እሴር የደብረ ጸባዖት አለቃ በዘመናቸው ሁሉ እስኪሞቱ ድረስ ከውሃ
በቀር ወይን (ሌላ መጠጥ) ጠጥተው ! በምንጣፍ ተኝተው የማያውቁ
ይልና "በዓለ ሕርመት አስቄጥሳዊ" ይላቸዋል(2)።
፫. አባ ተክለ ማኅበር መምህረ ነገረ ነገሥት (3) ።
፬. እርጎንዮስ

ጸሐፊው የመንግሥቱን ባለሥልጣኖችና የጦር አለቆቹን ወደ ጐን ትቶ
የቤተ ክህነቱን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ብቻ ማንሣቱ ራሱ የቤተ ክህነት ሰው
ከመሆኑ በቀር በዚያን ጊዜ ወይም በርሱ ዘንድ ከፍተኛ ሆነው የሚታዩት እነርሱ
ብቻ ስለሆኑ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ አሚር ኑር የዓፄ ገላውዴዎስን የተቆረጠ ጭንቅላት ይዞ በደስታ
ሐረር ሲገባ በርሱና ገላውዴዎስን ገድሎ ለማግባት ውል በገባላት በድል ወን
በራ መካከል ታላቅ ደስታ እንደሚፈጠር የታወቀ ነው ። ይህ የድል ወንበ
ራና የአሚር ኑር ደስታ ከ፲፰ ዓመት በፊት የግራኝ አህመድ ጭንቅላት በተቆረጠ
ጊዜ በንግሥት ሰብለ ወንጌልና ባፄ ገላውዴዎስ ዘንድ ከነበረው ደስታ ጋር ተመሳ
ሳይ ነው ። አሁን ደግሞ በገላውዴዎስ ሞት ኀዘን ፊቱን ወደ ንግሥት ሰብለ ወን

(2) ወጸንዓ ጥቀ ቀትል በይእቲ ዕለት እስከ ገልባቦ ለፀሐይ ጢሰ እሳተ ፀብእ ከመ ግዘፈ ጊሜ ። ጉንዘ
ልማን ገጽ 102 ።
(1) አስቄጥሳዊ ማለቱ በላይኛው ግብፅ የአስቄጥስን ገዳም ገድመው ከዚህ ዓለም ተድላ ደስታ
ርቀው ከኖሩት ከአባ እንጦንዮስና ከአባ መቃርስ ጋር ለማመሳሰል ነው ።
(3) የቤተ መንግሥትን ወግና ሥርዓት የሚያውቁ ለማለት ነው ። ጉንዘልማን ያላተመው ዜና መዋ
ዕል ገጽ 105 - 107

ጌልና ወደ ዘመዶቻቸው ሲመለስ ይታያል ።

ስመ ጥሩዪቱ ድል ወንበራ ቀድሞ ያባቷን የማኅፉዝን ሞት በባሏ በግራኝ አህመድ አማካይነት የማኅፉዝን ቀጥተኛ ገዳይ አባ እንድርያስን በማስገደል አስገ ዳዩን ዓፄ ልብነ ድንግልን ከገር ወዳገር በማሳደድ እንደተበቀለች ፤ አሁን ደግሞ የባ ሏን የግራኝን ገዳይ ገላውዴዎስን ባዲሱ ባል በኑር እጅ ስትበቀል ይታያል ። ከመ ዠመሪያ ከ፲፰፻፲፱ ዓ. ም. ዠምሮ እስካሁን ያደረገችውን ስንመለከት የተናገረች ውን ስንሰማ ሴትዮዋ እንደነ እቴጌ ጣይቱ የምትቆጠር ኃይለኛ ሴት እንደነበረች ይታወቃል ።

ታሪከ ነገሥት የምንለው የጸሐፊው ስም የማይታወቅ የተጻፈው ሁልጊዜ በመሠረቱ አንድ እየሆነ በአነጋገር ስለሚለያይ ከሥር እስከ መጨረሻ ያለው ያንድ ሰው ጽሑፍ ሳይሆን የሁለት የሦስት ሰው እጅ ለየብቻ የጻፈው መሆኑ ይታ ወቃል ። በዚህ ምክንያት ስለጭንቅላታቸው አቀራረጥና ሐረር ሄዶ ስለመሰቀሉ በልዩ ልዩ መንገድ ሲተረክ ይታያል ።

አንደኛው ጸሐፊ «የንጉሡን ራስ ቆርጠው አዳል ወስደው በእንጨት ላይ በሰ ቀሉት ጊዜ ለሦስት ዓመት ዝናም በአዳል አገር (ሐረርጌ) ሳይዘንም በመቅረቱ በኋላ ነጋዴዎች የንጉሡን ጭንቅላት ከተሰቀለበት አውርደው የቅዱስ ገላውዴ ዎስ መቃብር ባለበት በአንጾኪያ ወስደው ቀበሩት የተረፈው አካላቸው እስከ ዛሬ በተድባበ ማርያም ይገኛል« ሲል (1) ሁለተኛው »ራሱን ግን ከሀዲው ኑር ቆርጦ ወደ አዳል ወስዶ በደጃፉ ስለሰቀለው በኤልያስ ምግብ የተነሣ ዝናም ቆሞ እንደነ በረ የገላውዴዎስን ጭንቅላት አካሉ ላይ እስኪመልሱ ድረስ ዝናም በአዳል አገር ቆመ« (2) ይላል ። በዚህ ዓይነት ራሳቸው ከአካላቸው ተገናኝቶ የተቀበረበትን የላ ይኛው በመዠመሪያ አንጾኪያ ከቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ካመለከተ በኋላ ቀጥሎ እስከ ዛሬ ዓጽማቸው በተድባበ ማርያም አለ ስለሚል ምና ልባት በመዠመሪያ ኤፍራሑታ ውስጥ ራሳቸው በሕይወታቸው ሳሉ ባሠሩት በስመ ሞግሼያቸው በቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን ከተቀበሩ በኋላ በሚቀጥ ለው ዘመን አጽማቸው ከኤፍራሑታ ወደ ቤተ አምሐራ ተዛውሮ በተድባበ ማር ያም ተቀብሮ ይሆናል ።

የዘመኑ ጸሐፊ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን አዋቂ እንደመሆኑ መጠን የሚጽፈውን ሁሉ በብሉይና በሐዲስ ከሚገኘው አድራጎት ጋር ሲያገናዝበው ይገኛል ። በዚህ ምክንያት «የገላውዴዎስ ጭንቅላት ከአካሉ እስከተገናኘበት ጊዜ ድረስ ዝናም

(1) . . . . . . ወመተሩ ርእሶ ወወሰድዎ ውስተ አዳል ወሰቀልዎ ዲበ ዕፅ ወኢዘንመ ዝናም ሠለስተ ዓመተ ወእምድኅረዝ ወሰድዎ ነጋድያን ለውእቱ ርእሱ ምቱር ወአብጽሕዎ ሀገረ አንጾኪያ ወተ ቀብረ በመቃብሪሁ ለቅዱስ ገላውዴዎስ ሰማዕት ዓቢይ ወዘተርፈሰ ሥጋሁ ሀሎ እስከ ይእዜ በተ ድባበ ማርያም . . . .

(2) . . . . . . ሰርዐሰሰ ኑር አላዊ መተራ ወወሰዳ ምድረ አዳል እንዘ ይትመየጥ ብሔሮ ወአንበራ ዲበ ጸቆኑ ወበእንተዝ ተርፈ (ቀረ) ዝናም ውስተ ምድረ አዳል ከመ ምግበ ኤልያስ እስከ አመ አግብ ዕዋ ለይእቲ ርእስ ኃበ ሥጋሃ እሜሃ ዘንመ በአዳል ዝናም ፡

ያኄ ገላውዴዎስ ትግልና የሕይወታቸው ፍጻሜ

ሲል ያነበብነው ኤልያስ በአጻል ሦስት ዓመት ቆሞ በተገናኘ ጊዜ ግን ዘነመ» ሲል ያነበብነው ኤልያስ

በአጻል ሦስት ዓመት ቆመ በተገናኘ ጊዜ ግን ዘነመ» ሲል ያነበብነው ኤልያስ ሦስት ዓመት ዘጋ የነቢዩን

ነቢዩ በእሥራኤል ንጉሥ በአክአብ ዘመን ዝናምን ለሦስት ዓመት ዘጋ የነቢዩን

ነቢዩ በእሥራኤል ንጉሥ በአክአብ ዘመን ዝናምን ለሦስት ዓመት ዘጋ ከሚባለው ጋር መገናኘቱ ነው (1) ።

ምግብ ግን ቁራ ከሰማይ ያመላልስለት ነበር ከሚባለው ጋር መገናኘቱ ነው (1) ።

ምግብ ግን ቁራ ከሰማይ ያመላልስለት ነበር የተጻፈውን አብራርቶና አሟልቶ እን

ሌላ ሦስተኛ ጽሑፍ ደግሞ ከዚህ በላይ የተጻፈውን አብራርቶና አሟልቶ እን

ሌላ ሦስተኛ ጽሑፍ ደግሞ ከዚህ በላይ ሐረር በር ወስዶ እንደሰቀለው

ደዚህ ይላል «ኑር ያኄ ገላውዴዎስን ራስ ቆርጦ ሐረር በር ወስዶ እንደሰቀለው

ደዚህ ይላል «ኑር ያኄ ገላውዴዎስን ራስ ቆርጦ ድል ወንበራ አዋቂዎቿን ብትጠይቅ የከ

ዝናም ጠፍቶ ረሃብ ሆነ የዚህን ምክንያት ድል ወንበራ አዋቂዎቿን ብትጠይቅ የከ

ዝናም ጠፍቶ ረሃብ ሆነ የዚህን ምክንያት ስለአሰቀልሽ ፈጣሪ ተቆጥቶ ነው

ርስቲያኑን ንጉሥ ጭንቅላት ሐረር በር ላይ ስለአሰቀልሽ ፈጣሪ ተቆጥቶ ነው

ርስቲያኑን ንጉሥ ጭንቅላት ሐረር በር ላይ እስወርዳ ወደ አንጾኪያ በነጋዴ

ብለው መለሱላት ከዚያ በኋላ ጭንቅላታቸውን አስወርዳ ወደ አንጾኪያ በነጋዴ

ብለው መለሱላት ከዚያ በኋላ ጭንቅላታቸውን ሲል ያመለክታል ።

ዎች እጅ ላከችው ፤ የቆመውም ዝናም ዘነመ» ሲል ያመለክታል ።

ዎች እጅ ላከችው ፤ የቆመውም ዝናም ዘነመ» ምክንያት መሆኑን እያነሣም

በእርሳቸው ጭንቅላት መቆረጥና መሰቀል ምክንያት መሆኑን እያነሣም

በእርሳቸው ጭንቅላት መቆረጥና መሰቀል ምክንያት እሲዞ እንደተመለሰ በአገሩ ላይ ከፍ ያለ

እንጂ ኑር የዓፄ ገላውዴዎስን ጭንቅላት እሲዞ እንደተመለሰ በአገሩ ላይ ከፍ ያለ

እንጂ ኑር የዓፄ ገላውዴዎስን ሥጋ እስከ መብላት መድረሱን

ረሃብ ተነሥቶ እናት የልጅዋን ፤ ባል የሚስቱን ሥጋ እስከ መብላት መድረሱን

ረሃብ ተነሥቶ እናት የልጅዋን ፤ ባል የሚስቱን ሥጋ አቡበከር ኢብን መሐመድ

ሊቁ አንሪኮ ቼሩሊ ከዚህ በፊት ስሙን ከጠቀስነው አቡበከር ኢብን መሐመድ

ሊቁ አንሪኮ ቼሩሊ ከዚህ በፊት ስሙን ከጠቀስነው ቃሉም ከዚህ በፊት ካወሳነው

ጽሑፍ ላይ ወደ ኢጣልያ ተርጉመውት ይገኛል ። ቃሉም ከዚህ በፊት ካወሳነው

ጽሑፍ ላይ ወደ ኢጣልያ ተርጉመውት ይገኛል ። ነው ።

ጋር በትክክል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ጋር በትክክል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው የሙጃሂድ ልጆ ልቡሉ ኑር

«ከርሱ በኋላ (2) የአማኞች መስፍን ጌታችን የሙጃሂድ ልጆ ልቡሉ ኑር

«ከርሱ በኋላ (2) የእግዚአብሔር ምሕረት በ፱፻፸፭

በሂጅራ የዘመን አቈጣጠር በ፱፻፶፬ ዓመት (3) የእግዚአብሔር ምሕረት በ፱፻፸፭

በሂጅራ የዘመን አቈጣጠር በ፱፻፶፬ ዓመት (3) ዓረብ አለፈ (4) ።

ዓመት በረቢ አል አዋል ወር በወሩ በመጨረሻው ፪ኛISIC ቀን ዓረብ አለፈ (4) ።

ዓመት በረቢ አል አዋል ወር በወሩ በመጨረሻው ፪ኛ ቀን መልካም ጠባይ ፍርዱ

ኤሚሩ ልዑል አምላክ ምሕረቱን ይስጠውና በሕይወቱ መልካም ጠባይ ፍርዱ

ኤሚሩ ልዑል አምላክ ምሕረቱን ይስጠውና እርሱም ሁለተ

ትክክለኛ በተለይ በመንፈሳዊ ረገድ የተመረጠ ችሎታ ነበረው ። እርሱም ሁለተ

ትክክለኛ በተለይ በመንፈሳዊ ረገድ የተመረጠ ከሀበሻው ንጉሥ ጋር

ኛው ድል አድራጊ ስለሆነ . . . . . እጥናፍ ሰገድ ከሚባለው ከሀበሻው ንጉሥ ጋር

ኛው ድል አድራጊ ስለሆነ . . . . . ወደ ሰዓድ ኤድ ዲን

ተዋግቶ ገደለው ። ጭንቅላቱንም ቆርጦ ሰለባውን እንደያዘ ወደ ሰዓድ ኤድ ዲን

ተዋግቶ ገደለው ። ጭንቅላቱንም ቆርጦ ኤሚሩ የሀበሻን

መጣ (5) ። የዚህን ንጉሥ ጭንቅላቱን እኔ ራሴ አይቸዋለሁ ። ኤሚሩ የሀበሻን

መጣ (5) ። የዚህን ንጉሥ ጭንቅላቱን እኔ ራሴ ተመለሰ ።

አገር ከዘረፈ በኋላ ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ከዚህ ውጊያ እንደተመለሰ ባገር ላይ ታላቅ ረሃብ ተነሥቶ አንድ ልክ በቆሎ

ከዚህ ውጊያ እንደተመለሰ ባገር ላይ ታላቅ ረሃብ ተነሥቶ አንድ ልክ በቆሎ ፤ የቀንድ ከብት

አሥራ ሁለት አሽራፍ ፤ አንድ ልክ ጨው ሃያ አምስት አሽራፍ ፤ የቀንድ ከብት

(1) ፩ኛ ነገሥት ምዕ. 17 ቊ. 6 - 8 ፤ የያዕቆብ መልእክት ምዕ. 5 ቊ. 17 - 18

(2) ከግራኝ አህመድ በኋላ ማለቱ ነው ።

(3) ፱፻፶፬ መሐመድ ነቢዩ ከተወለደ ዠምሮ ያለው ዓመት ነው ። በአውሮፓ ፲፭፻፵፩ - ፲፭፻፵፯ መካ ።

(4) በሂጅራ ፱፻፸፭ ዓመት እንደ እው. ቊ. ፲፭፻፷፯ መስከረም ፮ ይሆናል (በኛ ፲፭፻፶፱ ዓ. ም.)

መሆኑ ነው ።

(5) ሰዓዲን ሲል መላውን ሐረርጌን አዳልን ሁሉ የወላስሞች ግዛት የሆነውን ሁሉ በመሐመድ አቡል

በረከት ሰዓድ ኤድ ዲን ስም በነአርቄ በድላይ አባት ስም ባጭሩ የሰዓዲን አገር እንደሚለው

ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

ሦስት መቶ አሽራፍና ከዚያም በላይ አወጣ (1) ።

ጋሎችም በየአገሩ ሕዝቡን ይዘርፉ ነበር ። በዚህ የችግር ጊዜ እምላክ ለሕዝቡ ትዕግሥትን ሰጠ ። ኤሚር ኑርም ደህና አድርጎ ታገሠ ። ሃይማኖቱም የበለጠ ጠንክሮ የሰው ሀብት እንዳይነካም አስከበረ ። አንዳንዶቹ የልጆቻቸውን አንዳንዶቹም የሚስቶቻቸውን ሥጋ በሉ ። አንድ ቀን እኔው ራሴ ባለሁበት ገማል ኤድ ዲን የሚባለው ቃዲ ባስቻለበት ሸንጎ ላይ አንድ ሰው እንደታሠረ ሸክም ተሸክሞ ቀረበ ። አሥሮ ያመጣው ሰው እንደዚህ አለ "ይህ ሰው ሚስቱን ገድሎ ለመብላት የአካሏን መለያልይ ከፋፍሎታል" ። ሸክሙ ወርዶ ቢታይ እንዲት ሴ እንደ አንድ እንደምትበላ ፍየል አካሏ ተቆራርጦ ተገኘ ። ዳኛው ተገርሞ የተቆራረጠው የሴትዮዋ ሥጋ እንዲቀበር አዘዘ ፤ በሌላ ቀንም ይኸንን የመሰለ ነገር ደርሶ ነበር ። ለእግዚአብሔር ሆሳዕና ሕዝቡን በፈቀደው ዓይነት ለሚፈትነው . . . . . አሚር ኑር በበሽታው ዘመን ሞተ ፤ የሞተበትም ምክንያት የዚሁ በሽታ ጠንቅ ነው ። እግዚአብሔር ይቅርታና ምሕረቱን ያድርግለት . . . . . » (2) ።

በዚህ ምክንያት ይህ አቡበከር መሐመድ በዘመኑ ላይ ተገኝቶ የንጉሡን ጭንቅላት ተመልክቶ የረሃቡንም መጠን በዚህ ዓይነት ተርኮት ስለሚገኝ ዓረብኛው ጽሑፍ ከታሪክ ነገሥታችን አጻጻፍ ጋር በመሠረቱ ተስማምቷል ። የኛ ጸሐፊ ረሃቡ የተነሣበትን ምክንያት ባዔ ገላውዴዎስ ጭንቅላት መቆረጥ የረሃቡም ጊዜ የቆየበትን ፫ ዓመት ያደረገውን አ፩፲፫ከር የጻፈውና ቼሩሊ የተረጐሙት የረሃቡ አመጣጥ በዚህ ምክንያት መሆኑን ሳያረጋግጥም የጭንቅላቱንም ፍጻሜ ሳይናገር ከዚህ በላይ ያለውን ብቻ አመልክቶ ይዘጋል ። ይኸንንም የማይልበት ምክንያት በጭንቅላቱ መቆረጥ የተነሣ ረሃብ ተነሣ የተባለ እንደሆነ እንግዲያው አላህ የክርስቲያኖቹን ንጉሥና ሃይማኖታቸውን ይወዳል የሚል ግምት በእስላሞቹ መካከል እንዳይፈጠር ለመጠንቀቅ ይሆናል ። እኛም በዚህ ዘመን ያለነው የረሀቡን ምክንያት ልናረጋግጥ አንችልም ።

በኛ በኩል ታሪክ ነገሥቱ ኑር የተቆረጠውን የንጉሡን ጭንቅላት ይዞ ወደ አዳል ተመለሰ ብሎ የረሃቡን የጭንቅላታቸውን ወደ እንጾኪያ መመለስ ከተረከ በኋላ ጦርነቱ በሆነና ንጉሡ በተገደሉ በሦስተኛው ቀን በሕይወት ያለ አንድ ሰው ጦርነት ወደተደረገበት ሥፍራ ሄዶ ሬሳቸውን ወድቆ ማግኘቱን አንዱ አካላቸው ከሌላው ተጠጋግቶ ስለነበረና በሌላ ቀን ስለሚያውቃቸው (3) ለይቶ በነጭ ልብስ

(1) ልክ ያልሁት ቼሩሊ una misura............ ያሉትን ነው ። አሽራፍም የዘመኑ መገበያያ ሸርፉ ራፊ ገንዘብ ነው ። 22 መሐለቅ አንድ አሽራፍ 3 አሽራፍ አንድ ዶላር Foot-steps-BURTON. ገጽ 334

(2) La letteratura etiopica - Enrico Cerulli ገጽ 135 - 136 ። L'Islam di ieri e di oggi ገጽ 156 - 158

(3) ግዕዝኛው ወረከበ በድኖ ግዱፈ ወእእመሮ ዘተግዕት አሐዱ ለአሐዱ መለያልይሁ በከመ የአምሮ ቀዳሚ ይላል ።

(ለንዱናት) ገንዞ እንደቀበራቸው ይገልጽና ከዚሁ አያይዞ ገላውዴዎስ ሲሞቱ ሕዝብ ሁሉ በያለበት እንደተበተነ ፤ ግማሹም እየተዋጋ እንዳለቀ ፤ ሰው ሁሉም ስለርሳቸው ሞት በየቤቱ ሚስቱና ልጁ እንደሞተበት ያህል በዋይታና በመሪር ለቅሶ እንዳለቀሰ ፤ በእርሳቸው ሕይወት ጊዜ ባገር ላይ ብርሃን እንደነበረ በሞታቸው አገር እንደ ጨለመ አስፋፍቶ ይጽፋል (1) ።

የዓፄ ገላውዴዎስን ዜና መዋዕል የጻፈው ካህን ባንድ ወገን ረዘም አድርጎ በመጻፍና በአጻጻፍ ስልት ካለፉት ስለሚሻል በሌላ ወገን የአውሮፓውያንን ቀን አቈጣጠር ከኢትዮጵያ ቀንና ዓመተ ምሕረት ጋር እያገናዘበ ስለሚጠቅስ የውጭ አገር ትምህርት በመጠኑም ቢሆን የቀሰመ መምሰሉን ከዚህ በፊት አመልክተናል። ከዚሁ ጋር ደግሞ ስለ ንጉሡ ጠባይ በዝርዝር ስለሚጽፍ ስለ አሟሟታቸው ደግሞ በጣም ተበሳጭቶ በገዳያቸው በአሚር ኑርና ባባቱ በሙጃሂድ ቤተሰብ ፤ በሞቱበት ቀን ላይ እንደዚሁም በነርሱ አገር ላይ እርግማን ስለሚያወርድ አብሮአቸው የኖረ ባለሟላቸው ይመስላል ።

ከዚህ በፊት ስለንጉሡ አስተዳደግ ስለ ደግነታቸው ስለጠባያቸው የጻፈውን አንብበናል ። ከዚያው አከታትሎ ለወገናቸው ላገራቸውና ለሃይማኖታቸው ሲሉ ቁርጠኛ አሟሟታቸውን ፤ ሕዝባቸውን ከዘረፋና ከሞት ለማዳን ሲሉ የራሳቸውን ሕይወት መሠዋታቸውን ፤ የርሳቸው ሞት በሕዝባቸው ላይ የጣለውን ኀዘን ፤ ሕዝቡ እንደ ግል ቤተሰቡ እንዳለቀሰላቸው ባጭሩ የርሳቸው ሞት ባገር ላይ የኀዘን ጨለማ እንደጣለ አመልክቷል ።

የኝህ ንጉሠ ነገሥት አሟሟት ራሱን ጸሐፊውን በጣም ከኀዘን ላይ ጥሎት «. . . . . . ጌታዬ ማር ገላውዴዎስ የሞተባትን ቀን ምን ልበላት ? ችግረኞች የተወለዱበትን ዕለት እንደሚረግሙ ልርገማትን ? ወይስ ከቍጥር ውጭ አድርጌ ውድቅ ላድርጋትን ?» በማለት ገላውዴዎስ ስለሞቱባት ቀን ለመርገምም ወይም ከቀን ውጭ ለማድረግ በመቸገሩ ራሱን ይጠይቃል (2) ።

፪ኛ ከዚሁ አያይዞ የገዳያቸውን የሙጃሂድን ቤተ ሰብ አገሩንም ጭምር እንደዚህ ሲል ይረግማል «. . . . . ጌታዬን ገላውዴዎስን የገደለው በቤቱም በውጭም በጉዞውም ሲወጣም ሲገባም የተረገመ ይሁን ፤ የሠራው ሁሉ ወይኑን በረዶ ፍሬውን ተምች ይምታበት ፤ መሬቱ ዘር አይስጥ ፤ በጎቹ የሚበሉት ይጡ ። ላሞቹም ከበረት ይጥፉ ። ልዑሉና ክቡሩ እግዚአብሔር የሙጃሂድን ቤተሰብ እስከ አንድ ሺ ትውልድ ድረስ ይበቀል . . . . . .» (3) ። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ «. . . . . . . ወዮልን
)

(1) በኀዘን ማለቱ ነው ።

(2) ይቤ በዓለ መጽሐፍ ይምሐር እግዚአብሐር ወይማህሎ ፡ ምንተ እብላ ለዕለት ዘያእቲ ዕለተ ሞቱ ለእግዚእየ ማር ገላውዴዎስ ፡ ይደልወኑሁ እርግማ ከመ ዕለተ ልደቶሙ ለጽዑራን አው ይከውንኑሁ እረስያ ውጽእተ እምኍልቍ . . . . . . ኍንዘልማን ገጽ 108

(3) . . . . . ይትበቀሎ እግዚአብሔር ክቡር ወልዑል እስከ እሠርቱ ምእት ትውልድ ለቤተ ሙጃሂድ ፡ ወየአዝዝ ዝናመ ወጠለ ከመ ኢይረዱ ዲበ አድባሪሁ ወይረሲ ሎቱ መከፈልተ ሐመዳ ወአስሐትያ . . : . . . . ገጽ 109 ።

የጧት ንጋት መልሶ ጠለቀ (ጨለመብን) የማታ ኮከባችንም ጠፋብን» እያለ በግ ዕዝ ከአሌፍ ዠምሮ እስከ ታው ድረስ ባሉት በ፳፪ የዕብራውያን ፊደሎች እየለየ በግ ጥም መልክ ጥልቅ ኀዘኑን ይገልጣል ። በሙሉ ጽሑፉን ለማስፈር ስለሚበዛ የመ ዠመሪያውን የአሌፍን የጠቀስነውን በግርጌ አመልክተን የቀረውን ትተነ ዋል (1) ።

በዚህ ምክንያት በጽሑፉ ውስጥ የንጉሡ ነገሥቱን ጠባያቸውን ዕድገታቸ ውን ሞያቸውን በቀጥታ ከመጻፉ በቀር አልፎ አልፎ "እግዚእየ - ጌታዬ" ስለ ሚል ከዚህ በፊት እንዳልነው አብሮአቸው የኖረ ባለሟል አሽከራቸው ወይም ጸሐፊ ትእዛዛቸው መሆን አለበት ።

በተረፈ ከዚያ ወዲህ ደራሲው እገሌ ነው ለማለት የማይቻል ስለዓፄ ገላውዴ ዎስ አሟሟት ሁለት ዓይነት የአማርኛ ግጥም አለ ። አንደኛው ፋሲካን ሳይውሉ ዓርብ የስቅለት ለት መሞታቸውን እንደዚህ ሲል ያወሳል ።

ዓፄ ገላውዴዎስ ጌታን ተከተለ ፤
ፋሲካውን ሳይውል ዓርብ ተሰቀለ ፤
ጌታውም ሳይረሳው የፋሲካ ለታ ፤
አስጠርቶ አበላው ከጧት እስከ ማታ ።

ሁለተኛው ጭንቅላታቸው ከሸዋ ወደ ሐረር ከዚያ ወደ አንጾኪያ መጥቶ ማረ ፉን ከዮሐንስ መጥምቁ ዙረት ጋር በማነጣጠር እንደዚህ ይላል (2) ።

ዓፄ ገላውዴዎስ እንደ ዮሐንስ ፤
ባሕር ዳሩን ዞሮ ሸዋ ሲመለስ ፤
አንጾኪያ ታየ ብርሃንን ሲለብስ ።

ሁለቱም ያማርኛ ግጥሞች እንደፊተኛው በዚሁ በያዝነው በ፳ኛው እጅግ ቢርቅ በ፲፱ነኛው መቶ ዓ. ም. ላይ ታሪካቸውን ያነበበ ሐዲስ አዋቂ ሊቅ የገጠ መው ነው እንጂ በሞቱበት በ፲፮ኛው ወይም በ፲፯ - ፲፰ኛው ዘመን የተደረሰ ግጥም አይደለም ። የነዚህ ዘመናት ግጥሞች ይኸን በመሰለ አማርኛና ቅርጽ አይሳ ኩም ።

(1) አሌፍ - ቅትለተ ነፍሱ ለገላውዴዎስ እግዚእየ መኑ ላዕለ ነፍስየ እም አግብአ ወመኑ እምረሰየ ሊተ ከመ እዙን ውዱቀ ብእፍአ ወይ ለነ አሌ ለነ ኮከበ ጽባሕ አእመረ ምዕራቢሁ ወኮከበ ምሴ ትነ ጠፍአ . . . . . . . ገጽ 109 - 110

(2) ማቴዎስ ምዕ. 3

## ምዕራፍ ፻፶፬
## የአሚር ኑርና የግራኝ አህመድ ተከታዮች ፍጻሜ

የአባቱንና የወገኖቹን
አሚር ኑር ድል ወንበራን ለማግባትም ይሁን ወይም የአባቱንና የወገኖቹን
ደመኛ ለመበቀል ይሁን ደህና አድርጎ ተዘጋጅቶ መጥቶ እንደርሱ ያልተዘጋጁትን
ንጉሠ ነገሥት ተዋግቶ አሸንፎ ገድሎ ጭንቅላታቸውን አስቆርጦ ወደመጣበት
ወደ ሐረር ከመመለስ በቀር እንደ ሹመት አባቱ እንደ ግራኝ አህመድ ከድሉ በኋላ
ወደፊት ገፍቶ ኢትዮጵያን ለመያዝም ለመግዛትም ምኞት አላደረበትም ።
ምኞቱንም ያጠፋበት ባንድ ወገን ውጊያው ቀንቶት ከጦርነቱ እንደተመለሰ
ባገር የተነሣው ረሃብና በሽታ ባንድ ወገን የጋሎች ወረራ ነው ። በሌላው ወገን
እንደ ዓፄ ገላውዴዎስ ያለ የአርበኛ ንጉሥ አመካከትና በጠቅላላው መከራና ጦር
ነት ቢበዛበትም ዝግንቱ ያገሩና የሃይማኖቱ ፍቅር የማይበርደው የክርስቲያና
ዊው ሕዝብ የማይቋረጥ ተጋድሎ ነው ። ይኸው ሕዝብ ለአገር ነፃነት ከእስላሞቹ
ጋር በጦር መሣሪያ እየተዋጋ ስለ ሃይማኖቱ ደግሞ በፖርቱጋል ፣ በኢስፓኝ ፣ በፈ
ረንሳዊ መንግሥታት ከተደገፈው ከሮማ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ጋር ያደረ
ገውን የነገርና የክርክር ጦርነትና ፍጻሜውን እንብበናል ።
ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጦር ርዳታ ለማግኘት ሲል ሃይማኖቱን የማይ
ሸጥ ፣ በድካምና በማያቋርጥ ውጊያ ደግሞ ያገሩን ነፃነት የሚከላከል ጠንካራ ሕዝብ
በመሆኑ ሁለቱንም እንደጨበጠ ከሁለቱም በኩል የሚነፍሰውን ውሽንፍር እንደ
ተሸከመ እስከዚሁ ጊዜ ደረሰ ። ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳልነው በኢትዮጵያ እንዳ
ንድ የመከራ ዝናም አልፎ አልፎ በሚወርድበት ወይም የመከራው ደመና እየከ
በደ በሚታይበት ጊዜ ባንድ በኩል እግዚአብሔር የመዳኛ ብርሃንና መንገድ ለሕ
ዝቡ ይከፍትለታል ። ባሁኑ በገላውዴዎስ ሞት እስላሞቹ የልብ ልብ በቅቷቸው
ወደ ፊት እንዳይገፉ እነሆ ባል ሚስቱን እናት ልጅዋን እስኪበሉ ድረስ ጽኑ ረሃብ
መነሣቱ ከጋሎች ተዋጊነት ጋር ተጨምሮ አግዷቸዋል ማለት ነው ።
በዚህም በኢትዮጵያ በኩል ዓፄ ገላውዴዎስ ሲሞቱና ወንድማቸው ዓፄ
ሚናስ አድማስ ሰገድ (1) ተብለው ሲነግሡ የያዙትን ከማጥበቅ በቀር ወደ ሐረርጌ
ዘምተው ኑርን በመውጋት የወንድማቸውን ደም አልተበቀሉም ። በቀሉም ቢቀር
የጥንት አባቶቻቸው እነ ዓፄ ዓምደ ጽዮን እነ ዘርዓ ያዕቆብ ያስገበሩትን የአዳልን
ግዛት ለማስገበር ለጊዜው አልቻሉም ።
የዚህም ምክንያት እንደዚያው በኑር በኩል ካለው ችግር ተመሳሳይ የሆነ በዚ
ህም በክርስቲያኑ ንጉሥ ባፄ ሚናስ በኩል ይነስ ይብዛ መኖሩ የታወቀ ነው ።
በዚህም ላይ ከሚናስና ከልጁ ከሠርፀ ድንግል ወዲህ የመንግሥቱ መደብ
ከሸዋ ወደ ጐንደር ተዛውሮ ነገሥታቱ በዚያው ስለተቀመጡ በሀገሩ ርቀት በሐረ
ርም ዙሪያ ወታደር ማስቀመጡ በረሃነቱ የስንቁና የመገናኛው ነገር ተጨማ

(1) ወናግ ሰገድም ተብለዋል

ምር እስከ ዓፄ ኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ያሉት ኃያላን ነገሥታት እነሠርፀ ድንግል ፤ እነ አድያም ሰገድ ኢያሱ ቢሞክሩም ሐረርን የማስገበሩ ጉዳይ ከኢዮአስ ቀጥሎ ያሉትም ነገሥታት ኃይላቸው ፈጽሞ እየተዳከመ ስለሄደ የነርሱም ሥልጣን ወደ እንደራሴዎቻቸው ወደ ነራስ ስሑል ሚካኤል ወደነራስ አሊ ስለዞረ እንኳን ሐረርኄን ለማስገበር ከዚያ ቀረብ ያለውን የደቡቡን አውራጃ ችላ ስላሉት እንደ ሲዳሞ ፡ ከፋ ፡ ጅማ ፡ ወለጋ ያሉት እየተከፋፈሉ የየራሳቸውን ባላባት እያነገሡ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ቆዩ ።

ባለፈው ምዕራፍ እንዳነበብነው ግራኝ እንደሞተ የደቡቡን ክፍል እነአባስ ሲገዙ ከቆዩ በኋላ አሚር ኑር ከ፲፭፻፵፭ ዓ. ም. እስከ ፲፭፻፶፱ ዓ. ም. ድረስ (1) ሐረርኄን ሲገዛ ኖረ ። በሚገዛበትም ጊዜ የማዕርግ ስሙ እንደግራኝ አህመድ ይማም እንደወላስሞቹም ሡልጣን ሳይባል በአሚርነት ጸና ። ምክንያቱም ሡልጣንነት ከወላስሞች መወለድን ይማምነት ከግራኝ አህመድ መወለድ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትንና የጦርነት መሪ ለመሆን በምርጫና በትንቢት መደገፍ አለበት ። ኑር ቤን ሙጃሂድ ግን ምንም እንኳን ከግራኝ እህት ቢወለድ አባቱ ከሁለቱም ወገን ስላልሆን አሚር (ወይም ኤሚር) የሚባለውን የማዕርግ ስም እንደያዘ ኖረ ።

በዓረብ ፋቂህ መጽሐፍ ላይ እንደተመለከትነው የኤሚርነት ደረጃው ከሡልጣንም ከይማምም ከወዚርነትም የሚያንስ ላንድ ክፍል የጦር መሪ ወይም የአውራጃ ገዥ የሚሰጥ የማዕርግ ስም ስለነበረ ብዙዎቹ የግራኝ የጦር አለቆች ይኸንኑ ሥያሜ ይዘው ብዙ ጊዜ ከወዚሮቹ ካሉቴና ከአባስ በታች ሲተዳደሩ እንብበናል ።

ISIC

ይኸን ኤሚርነት ከመዠመሪያው ላይ ከነቢዩ መሐመድ በሴት በኩል ተወላጅነት ያላቸው የዓረብ መሳፍንት ይጠሩበት እንደነበረ አንዳንድ ጽሑፍ ያረጋግጣል (2)። የሆነ ሆኖ ኤሚር ኑር ዓፄ ገላውዴዎስን አሸንፎ ወደ ሐረር ሲመለስ ለድል አድራጊነቱ ተመጣጣኝ የሆነ የደስታ ጊዜ አልገጠመውም ። የዓረቡ ጸሐፊ የበሽታውንና የረሃቡን እንግሥ ወዲያው ከጦርነቱ ወደ ሐረር እንደተመለሰ መሆኑን እርሱም ምንም እንኳን ከውጊያው ወዲህ ፲ ዓመታት ቢቆይ የሞተው በዚሁ በተነሣው የበሽታ ሰበብ መሆኑን ያረጋግጣል ። ሞቶ የተቀበረውም እዚያው ሐረር ስለሆነ መቃብሩም በሻህ ሳሊህ አጠገብ በባብ ኤል ፋቱህ ጉብታ በፋንደላ በር ይገኛል ።

ሙሴ ኤንሪኮ ቼሩሊ ከዚህ በፊት በጠቀስነው መጽሐፋቸው ከነአል ኡመሪ መጻሕፍት ከዓረብኛ ወደ ኢጣልያንኛ በተረጐሙት ላይ የአማኞች መስፍን እየተባለ መጠራቱን ዕድገቱ ሐረር ስለሆነ በኋላም የግራኝን ደመኛ ገላውዴዎስን ስለገደለ የሐረርን ዙሪያ ቅጥር አሠርቶ ከተማዋን ከማሳመር ጋር በሕይወት ከክርስቲያኖችና ከጋሎች ጋር እየተዋጋ ስለሞተ ጻድቁ ኑር እየተባለ ከግራኝ አህመድ የበለጠ በአዳልና በሐረር የስመ ጥርነት ዝና እንዳለው ስለርሱም ልዩ ልዩ

(1) ፱፻፶፱ - ፱፻፸፯ ሂጅራ ፲፭፻፶፩ - ፶፪ - ፲፭፻፷፯ የአው. ቀ.
(2) በዚሁ ቃል . . . . . Dictionnaire littré............ ገጽ 601 ተመልከት ።

ግጥም እንደተገጠመለት ከማመልከት ጋር የተገጠመለትን ግጥም ከዓረብኛ ወደ
ኢጣልያንኛ ተርጉመውት ይገኛል ። በግጥሙ ላይ ለእስላሞቹ ሲል ከክርስቲያኖች
ጋር ቅዱስ ጦርነት ማድረጉ ፤ የንጉሡን ያጽናፍ ሰገድን ራስ መቁረጡ ፤ እርሱ
እንደ አንበሳ ሠራዊቱ እንደ ውኃ ማዕበል ሆነው በጠላት ልብና ደም ስር ላይ መሽ
በርን እንደሚያሳድሩ . . . . . እደጋ ባገር ላይ እንዳይደርስ ሕንፃ በማሠራቱ እግዚ
አብሔር እንደሚሸልመው . . . . . ተጽፎአል ። ያዬ ገላውዴዎስ ጸሐፊ ለጌታው
እንደገለጸው ይኸኛውም »ኑር የእስላሞች ዓምድ የከፉ ሁሉ (የበሽታ ሁሉ) ጠል
ሰም (መፍትሔ) ስለሆነ ዓይኔንም ነፍሴንም ብሰጠው እወዳለሁ . . . . .« በማለት
የጋለ ምኞቱን ያቀርብለታል (1) ።

ዓዬ ገላውዴዎስን የሆነ ሆኖ አሚር ኑር ከአባስ ወዲህ ሰባት ዓመታት ያህል በሐረር እንደገዛ በዚሁም
ካሸነፈ በኋላ ፰ ዓመት በድምሩ ፲፭ ዓመታት ጋሎች ጋር እየተከላከለ
ዘመን የኢትዮጵያን መንግሥትና እርሱን ከሚዋጉት ሥልጣን ለመያዝ በግራኝ
በመካከሉ በተነሣው በሽታ ታሞ ከሞተ ወዲህ የርሱን ሥልጣን ለመያዝ በግራኝ
አህመድ የቅርብ ተወላጆች መካከል ጠብ ከሆን በኋላ ላጭር ጊዜ እርሱ ይደግፈ
ውና ባሪያው የነበረው የሀበሻው ተወላጅ ኡስማን የሚባለው ሥልጣን ይዞ ሁለት
ዓመት ገዛ ። ነገር ግን በሀበሻው በኡስማን ላይ የቀድሞ የገዥዎች ቤተሰቦችና የግ
ራኝ ተወላጆች ከጋሎች ጋር ወዳጅ ሆኖ ተስማምቷል ፤ የደሀ ገንዘብ ለራሱ ይሰበ
ስባል ፤ የእስላምን ልማድና ሕግ ያፈርሳል ብለው ስለተነሡበት እርሱ ቀርቶ የወ
ዚር አባስ ልጅ ጠልሃ ወረሰ ። ኡስማን አበሻው ከማለት በቀር ከዓረብኛ ወደ ኢጣ
ልያንኛ የተተረጐመው ጽሑፍ ሌላ ዝርዝር ስለማይሰጥ የዚህ የኡስማን ዘሩና
ወገኑ ከምን ክፍል መሆኑ በምን አኳኋን ከወገኖቹ ክርስቲያኖች ወደኑር ዞሮ እንደ
ሰለመ አይታወቅም ። ምናልባት በዚሁ በግራኝ የጦርነት ዘመን በምርኮ የሄደና
የእስላሞቹን ወግና ሥርዓት እየተማረ ያደገ ይሆናል ።

ከአባስ ልጅ ከጦልሃ (2) ቀጥሎ ከ፲፰፻፳፱ - ፲፰፻፴፮ ዓ. ም. እንደ አው. ቀ. ከገዛ በኋላ
ደግሞ መደዳውን ባሉት አምስት ዓመታት ኤሚሮቹ (የኑር ተወላጆች) ከገዙ በኋላ
እንደ አው. ቀ. በ፲፰፻፴፯ ዓ. ም. መሐመድ ኢብን ኢብራሂም ጋሻ የሚባል የግ
ራኝ ተወላጅ ይማም ተብሎ ሥልጣን ያዘ ።

በዚህ ጊዜ እነዚያ ከይፋት ዠምረው እስከ ግራኝ አህመድ መነሣት ድረስ
ሱልጣን እየተባሉ ደንበኛ ነጋሢ ሆነው ይገዙ የነበሩት የኛም የግዕዙ ታሪክ ነገ
ሥት ንጉሠ አዳል ወይም ንጉሠ ዕልዋን የሚላቸው በምዕራፍ ፴ እንደተመ
ለከትነው በግራኝ እጅ ሥልጣናቸው ተገፎ ለስሙ ሱልጣን እየተባሉ የከበሬታ
ሥልጣን ብቻ ይዘው እስከ አሚር ኑር ከዘለቁ በኋላ በአሁኑ ሰዓት ፈጽሞ ከሥል
ጣን ውጭ ሆነው ሙሉው ሱልጣን በነዚሁ ይማም በሚባሉት በግራኝ ተወላጆች

(1) Studi-Etiopici- I La lingua e la storia di Harar. ገጽ 35 - 36 ፤ 48 - 49 ። L'Islam di Ieri E Di Oggi. ገጽ 157 - 158 ፤ 168 - 169 ። 320 - 321 ፤

(2) የግራኝ አህመድ የወንድም ልጅ የወዚር አባስ ልጅ መሆኑ ነው ፤

ISIC



ከሐረር ኤሚሮች አንዱ አህመድ ኢብን አቢባክር (አቡበከር) ዘሩ ከላይ ከአሊ ኢብን ዳውድ የወረደ የገዛበት ዘመን እንደ አው. ቀ. ፲፰፻፶፪ - ፲፰፻፶፮ ዓ. ም. ፲፰፻፶፭ ዓ. ም. ሪቻርድ ባርተንን ተቀብሎ ያነጋገረ እርሱ ነው (ሥዕሉ ከባርተን መጽሐፍ)

እጅ ሆኗል ። የመጨረሻ ወላስማዊ ሱልጣን ከአሊ ዑመር ዲን በኋላ በራካት ኢብን
ኡመር ዲን (1) በኑር ዘመን ላይ በ፲፭፻፶፭ እንደ አው. ቀ. ከገዛ በኋላ የርሱ ዘር
በሥልጣን ከመከታተል እንዳቋረጠ ይታያል ።
ሙሴ አንሪኮ ቼሩሊ በዚሁ የሐረር ታሪክ መጽሐፋቸው እንዳመለከቱት
ቀድሞ በነአቡበከር ጊዜ (፲፭፻፲፱ ዓ. ም.) ከይፋት ወደ ሐረርጌ የተዛወረው የሱል
ጣኖቹ መደብ በአሁኑ ገኘ በይማም መሐመድ ኢብን ኢብራሂም ጋሻ ጊዜ (፲፭፻
፸፯ ዓ. ም. እንደ አው. ቀ.) ከሐረርጌ ወደ አውሳ ተዛወረ ። መሐመድ ኢብን ኢብ
ራሂምም ካፄ ሠርፀ ድንግል ጋር የተዋጋው ነው (2) ።
እንደዚህ ሆኖ አውሳ የተዛወሩት ይማም እየተባሉ ሲገዙ ሐረርጌ ያሉት
ኤሚር እየተባሉ እያስተዳደሩ ለይማሞቹ እየታዘዙ ቆይተው በመጨረሻ አሚር
አሊ ኢብን ዳውድ (፲፯፻፵፯ - ፲፯፻፹፪ ዓ. ም. እንደ አው. ቀ.) ከገዛ በኋላ የራሱን
ዘር በሐረርጌ ዙፋን ላይ ተክሎ የርሱ ተወላጆች ለአውሳዎቹ ሳይገብሩ ነጻ ሆነው
በአዳሎቹና በሱማሌዎቹ በጋሎቹም ላይ ገዥ ሆነው ሲያስተዳድሩ ኖሩ ። ከነርሱ
መካከል በሌላው ዘንድ እንደሚገኘው ደህናም መጥፎም አስተዳዳሪዎች እንደሚገ
ኙባቸው የታወቀ ነው ።
አገሩን ግብጾች እንደ አው. ቀ. ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ከመያዛቸው በፊት የነበረው
የመጨረሻው አሚር አህመድ ቢን አቡበከር (፲፰፻፵፪ - ፲፰፻፷፯ ዓ. ም.) ከሁሉ የበ
ለጠ በጋሎች ላይ የተደጋገመ ድል ቢያገኝም የበለጠ ጨካኝ መጥፎ ደም አፍሳሽ
ዕብሪተኛ በቀላል ኃጢአት የሞት ፍርድ እየፈረደ በአደባባይ ሰው ማስቀል ወይም
ማቃጠል እወንድ ላይ ተያዘች የተባለች ሴት ከውኃ ውስጥ አስጥሞ ማስገደል
ወይም ራቁቷን ማስገረፍ ይኸን በመሳሰለው ቅጣት ላይም ራሱ እየተገኘ በማየት
ይደሰት ነበር ይባላል ። በዚህ ምክንያት አስተዳደሩም ንግዱም የተበላሸ ነበር ።
በዚህ መካከል በግብፅ ከዲቭ እስማኤል በሚያስተዳድርበት ጊዜ የስዌዝ
ቦይ ስለተከፈተና መርከብ እንደልብ መተላለፍ ስለቻለ ከዲቭ እስማኤል በሰሜን
በኩል ኢትዮጵያን ለመውረር እንደተነሣ እንደዚሁም በራውፍ ፓሻ አዝማችነት
አንድ ክፍል ጦር ልኮ እንደ አው. ቀ. ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፰፻፸፭ ዓ. ም. ሐረርጌን
ያዘ ። ሕዝቡም የራሱን አስተዳዳሪ አሚር አቡበክርን በመጥላት ተመሮ ስለነበረ
የግብፆችን ወረራና ከወረራው ቀጥሎ የታየውን ከአቡበክር የተሻለውን አስተዳ
ደር በመፍቀዱ የመጨረሻ አስተዳዳሪ የነበረው አሚር ሙሐመድ ኢብን አሊ የግ
ብጾችን አስተዳደር መቀበል ግዴታ ሆነበት ። ነገር ግን የመጨረሻው ይህ አሚር
ባንድ ግብጻዊ ወታደር ተገደለ ይባላል (3) ።

(1) የሱልጣን ኡመር ዲን ልጅ ፤
(2) የኢት. ታሪክ ከዓፄ ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ ምዕ. 21 ገጽ 78 - 80
(3) L'Islam di ieri e d'oggi......... ገጽ 380 ።

## ምዕራፍ ፻፶፰

## የሐረርጌ ከኢትዮጵያ ጋር እንደገና መዋሐድ (፲፰፻፸፱ ዓ. ም.)

ይኸ ሁሉ ሲሆን ዓፄ ገላውዴዎስ ከሞቱ ፤ ወንድማቸው ሚናስና የሚናስ ልጅ ዓፄ ሠርፀ ድንግል ከነገሡ ወዲህ በተለይ ሠርፀ ድንግል በተቻለ መጠን በግራኝ ጊዜ ሄዶ ካባታቸው ከሚናስ በተለይም ከአርበኛው አጐታቸው ከዓፄ ገላውዴዎስ የተ ረፈውን የደቡብ ወረዳዎች ለማስለቀቅ ወደ እናርያ ወደ ጉራጌ ወደ ሐረር ግዛት ድንበር እየተዘዋወሩ በዘዴም በጦርነትም አገሪቱን በቀድሞው መልኳ ለማቋቋም ጥረዋል ። በዘመናቸውም ምንም የሐረርጌን ግዛት ማስለቀቅ ባይሆንላቸው ከይ ማም መሐመድ ኢብን ኢብራሂምና ከመሐመድ ኢብን ናስር ጋር ተዋግተዋል ።

ነገር ግን ከርሳቸው ወዲህ ቀጥሎ ባለው ጊዜ የመንግሥቱ መደብ ከሸዋ ወደ ጐንደር ፈጽሞ ስለዞረ ከዚህ በፊት እንዳወሳነው ፤

ሀ. በአገሩ ርቀት በመገናኛ እጦት ፤

ለ. ነዋሪ ወታደር ለማስቀመጥ ያገሩ በረሃማነት የስንቅ ማቀበሉ ችግር ፤

ሐ. ከልብነ ድንግል እወለዳለሁ የሚለው በኋላ ደግሞ ከሠርፀ ድንግል ቀጥሎ ልጃቸው ያዕቆብ ዙፋን ከወረሰ በኋላ በሌላ ዘርፍ የወረደው ሱስንዮስ መንግሥትን ከያዕቆብ በመውሰዱ ምክንያት የያዕቆብ ዝርያዎች በየጊ ጊዜው እየተነሡ የሱስንዮስን ተከታዮች ማወክ በየጊዜው ያዕቆብ ነኝ የያዕቆብ ልጅ ነኝ በማለት እየተነሡ ከነርሱ ጋር የሚደረው ጦርነት

መ. የፈላሾችና የጋሎች አልፎ አልፎ መሸፈት ፤

ሠ. በምጥዋና በሐማሴን በኩል የቱርኮቹና የግብጾቹ ማወክ የባሕር ነጋሾቹ አንዳንድ ጊዜ ከነርሱ መለጠፍ ፤

ረ. በማይመረመረው በክርስቶስ ባሕርይ ምክንያት ካህናቱ ግማሾቹ ካራ ዎች ፤ ግማሾች ቅባቶች ፤ የቀሩትም የጸጋ ልጆች እየተባባሉ በሚያመ ጡት የረቀቀ ክርክር ጉባዔ እየተደረገ ነገሥታቱ እነዚህን በመገላገል የሸፈተውን በመደምሰስ ሁሉም በየመልኩ ችሎታቸውን ኃይላቸውን ይኸን የመሳሰለው ጉዳይ ስለሚወስደውና ጊዜ እልሰጥ ስለአለ የአባቶቻ ቸው የነዓምደ ጽዮን ፤ የነዘርዓ ያዕቆብ ግዛት የነበረውን የሩቁን የሐረር ጌንና የአካባቢውን ግዛት የጐንደር ነገሥታት ከይማሞቹ ሆነ ከአሚሮቹ ተፋልመው ሊመልሱም እነርሱንም ባሉበት እንደተለመደ ለማስገበር አልቻሉም ።

ወደ መጨረሻውም ጊዜ እንኳን የሐረር ግዛት ሊጠቃለል የነገሥታቱ ሥል ጣን በ፲፰ው መቶ ዓ. ም. በእንደራሴዎቻቸው በነራስ ስሑል ሚካኤል እጅ ሲወ ሰድ ከቅርብ ያለው የሸዋው ክፍል ከጐንደር መንግሥት ተለይቶ በራሱ መስፍን ይተዳደር ዠመር ። በደቡብ ክፍል ያሉት የባሌ የአሩሲ የሲዳሞ የከፋ የወላሞ የጐማ የወለጋ የጐሬ የጅማ አገሮች ሁሉ በጐንደር የመንግሥቱ መዳከም አማዟ

ቸው በየራሳቸው ባላባት በነፃ አንዳንድ ጊዜም አንዱ የጐኑን እየጠቀለለ ይተዳ
ደሩ ዠመር ።

በዚህ ድካምና መከፋፈል መካከል ወደ መጨረሻ ጊዜ ደጃች ካሣ ከቋራ ሳይ
ታሰቡ ተነሥተው የየአውራጃውን መሳፍንትና መኳንንት በየተራ አሸንፈው ቴዎ
ድሮስ ተብለው ነገሡ ። የርሳቸውን መርሕና ምሳሌ ዓፄ ተክለ ጊዮርጊስና ዓፄ ዮሐ
ንስ እየተከተሉ በየተራ ነግሠው ኢትዮጵያን ወደ ጥንት አቅዋሟ ለመመለስ በዘ
መናቸው የተቻላቸውን ሠሩ ።

እንግዲህ ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የግብፅ መንግሥት እንደ አው. ቀ.
በ፲፰፻፷፰ ዓ. ም. ሐረርጌን ከያዘ በኋላ ኢትዮጵያንም ለመጠቅለል ወደ ዓፄ ዮሐ
ንስ በ፲፰፻፷፰ እና በ፲፰፻፷፱ ዓ. ም. እንደ አው. ቀ. ሁለት ጊዜ ጦር ልኮ ሲዋጋ
ሁለት ጊዜም ባፄ ዮሐንስ የሚመራው ጦር እያሸነፈ መለሰው ። ነገር ግን ቢሸነ
ፍም እንደተመኘው ኢትዮጵያን በሙሉ ወርሮ ከሐረር አገናኝቶ ግዛቱን ከሚዲቴ
ራኔ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ለማስፋት ያለው ሰፊ ዓላማ ተሰናከለ እንጂ ከኢትዮ
ጵያ ታሪካዊ ጠረፍ ከምጥዋም ከሐባብና ከከረን ከቦጐስና ከሐረርም ለጊዜው ሊነ
ቃነቅ አልቻለም ።

ዓፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ በዙፋናቸው ሊተካ የቻለ ልጅ ስለአልነበራቸው ባንድ
ጊዜ ውስጥ የርሳቸውን ዙፋን ለመውረስ በላስታ ዋግ ሥዩም ጐበዜ (ዓፄ ተክለ
ጊዮርጊስ) በትግሬ ደጃች ካሣ (ዓፄ ዮሐንስ) በሸዋ ንጉሥ ምኒልክ እንደተነሡ ለጊ
ዜው የመዠመሪያው ዋግ ሥዩም ጐበዜ ከቀሩት በርታ ስላሉ ተክለ ጊዮርጊስ ተብ
ለው ነገሡ ። ከርሳቸውም ጋር በመጨረሻ  ደጃች ካሣ ተዋግተው አሸንፈው ዮሐ
ንስ ተብለው በንጉሠ ነገሥትነት  ተቀብተው እንደነገሡ ታሪኩ የቅርብ ጊዜ ስለ
ሆነ በብዙዎች ዘንድ የታወቀ ነው ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ንጉሥ ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ ሞት ሦስት ዓመት ቀደም
ብለው ከ፲፰፻፶፯ ዓ. ም. ዠምረው ሸዋንና በሸዋ ዙሪያ ያለውን የጋላ አገር ወሎን
ጨምረው ይዘው እያስተዳደሩ በበኩላቸው እንዳፄ ቴዎድሮስ ተከታይ ምኒልክ
ንጉሠ ነገሥት የሚል ማኅተም እያተሙ ሸዋንና ወሎን ያስተዳድሩ ዠመር ። ላፄ
ተክለ ጊዮርጊስ እንደአልገበሩ ላፄ ዮሐንስም አልገብርም ብለው ከ፲፰፻፷፰ ዓ. ም.
እስከ ፲፰፻፸ ዓ. ም.  ፲፱ ዓመታት ያህል በነፃነት ከቆዩ በኋላ ዓፄ ዮሐንስ ጦር
ይዘው እስከ ደብረ ብርሃን ስለመጡ እርሳቸውም ለመመከት ከተዘጋጁ በኋላ በግል
ግልና በእርቅ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነቱን ደረጃ ላፄ ዮሐንስ ለቀው እርሳቸው
"ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ" እየተባሉ የደንቡን ያመት
ግብር ላፄ ዮሐንስ እየገበሩ በውስጥ አስተዳደራቸው ነፃ ሆነው ቀደም ብለው እንደ
ዠመሩት በግራኝ ጊዜ የተነጣጠሉትን የደቡብና የምዕራብ የኢትዮጵያን አውራጃ
ዎች ራሳቸውም እየዘመቱ የጦርና ያስተዳደር መኳንንቶቻቸውን እነራስ ዳርጌን
እነራስ ጐበናን ፡ እነደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣንን ፡ እነደጃች ወልደ ጊዮር
ጊስን እነደጃች ተሰማን እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን እነደጃች በሻህ አቦዬን
እነደጃች አሰፋው ዳርጌን በየመስመሩ እየላኩ የኢትዮጵያን ግዛት አስፋፉ ። ወደ

መጨረሻው ጊዜ መልሶ እስኪደፈርስ ድረስ ካዔ ዮሐንስም ጋር ልጃቸውን ወይ ዘሮ ዘውዲቱን በመዳር አባትና ልጅ ሆነው ተስማሙ ።

በጠቅላላው ዳግማዊ ምኒልክ በዚህ ዓይነት ከግራኝ አህመድ ወዲህ በግራኝ ወረራ ሰበብ ከእናት አገሩ በመለየት ተከፋፍሎ ለየብቻ የነበረውን የኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ አቅንተው ወደ ኢትዮጵያ መደረባቸውን የተረዳ አንድ ስሙ ሊታወቅ ያልቻለ ሊቅ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በመግጠም አመስግኗቸዋል ።

፩. የኢትዮጵያን ድንበር ግራኝ ቢያፈርስ ፤
ከነበረበቱ ድንበሩዋን ሊመልስ ፤
በወንጌል ተካሶ ያባ ዳኘው ፈረስ ፤
መስቀል አዞረበት እስከ ዳሩ ድረስ ።
፪. ያባ ዳኘው ፈረስ ሄደ ገሥገሠ ፤
ጣዖቱም ወደቀ መስጊዱም ፈረሰ ፤
የረከሰው አገር በርሱ ተቀደሰ ።
፫. የአምላክ ልማዱ ማዛወር ነውና ፤
በግራኝ የዘባው በምኒልክ ቀና ።
፬. ዳግማይ ምኒልክ ሆነ ቆስጠንጢኖስ ፤
የተቀበረውን እያወጣ በጢስ ፤
መስቀል አዞረበት ሃይማኖት እንዲፈርስ [sic] ፤
፭. የምኒልክ ፈረስ ምድሩን ጨረሰና ፤
ባሕር ተሻገረ ጉልበቱ ጠናና ።

ከዚህ በፊት እንዳልነው የግብፁ ገዥ ከዲቭ ኢስማኤል በራውፍ ፓሻ አዝማችነት እንደ አው. ቀ·ጥር በ፲፰፻፷፰ ዓ. ም. ሐረርን ከያዘ በኋላ ከራውፍ ፓሻ በ፲፰፻፸ ዓ. ም. ሪድዋን ፓሻ ከርሱም መሐመድ ናዲና አሊ ሪዳ ተከታትለው በሚያስተዳድሩበት ጊዜ የግብፅ ሁኔታ እንደዚሁም የዚያ ያስፈሪውና የታላቁ የቱርክ የሱልጣኖች መንግሥት በእንግሊዞችና በፈረንሳዮች በመስኮቦችም አነሣሥ በየጊዜው በመንዝንዝ እየተዳከመ ሄደ ። ኤኮኖሚውን እንግሊዝና ፈረንሳይ ይዘው ወደ ፊት አላራምድ አሉት ። እንደዚህ ያለ ታላቅና በያለበት የተስፋፋ መንግሥትም ወደፊት ካልተራመደ በግድ ወደኋላ ወደነበረበት መራመድ እንጂ ባለበት ሁኔታ መቆየት አይችልም ።

ስለዚህ ግማሹ ጦር በኢትዮጵያ ሰሜን ባዪ ዮሐንስ ከተሸነፈ በኋላ በሱዳንም ካገር ተወላጁ ውስጥ ነቢይም መሪም ሆኖ የተነሣው መህዲ በሱዳን የነበረውን የግብፅንና የቱርክን ጦር በውጊያ ካገሩ አስወጣ ። እንደዚሁም የግብፅ ጦር ከሱዳን ሲወጣ እንግሊዝ የግብፅንና የቱርክን አወዳደቅ እያደባ ጠብቆ ራሱ ከተተካ በኋላ ከምጥዋ ከሐባብና ከቦጎስ የቱርክና የግብፅ ጦር በሚወጣበት ጊዜ ይህ ክፍል ለር ስዎ ይመለሳል እያለ ባንድ ወገን ዓዔ ዮሐንስን እያጓጓ በሌላው ወገን ኢጣልያንን ጠቅሶ ይኸንኑ በታሪክ የኢትዮጵያ ክፍል የሆነውን የባሕር ነጋሽ ግዛት ኢጣልያኖች እንዲይዙት አደረገ ።

የግራኝ አህመድ ወረራ

በዚሁ ዓይነት የግብፅ ጦር ሐረርጌንም መልቀቅ ግዴታ ስለሆነበት የመጨረ
በዚሁ ዓይነት የግብፅ ጦር ሐረርጌንም መልቀቅ ግዴታ ስለሆነበት የመጨረ ትእ
ሻው ግብፃዊ ገዥ አሊ ሪዳ ፓሻ ከዋናው ገዥ ከከዲቭ ኢስማኢል በመጣለት ትእ
ዛዝ መሠረት በ፲፰፻፹፮ ዓ.ም. ግንቦት ፰ ቀን እ. አው. ቀ. ያገሩን ተወላጅ አሚር
አብዱላሂ የሚባለውን የመሐመድን ልጅ ለገዥነት ሾሞ እርሱ ጦሩን ጠቅሎ ወጣ ።
አሚር አብዱላሂ ከላይ ዘሩ የመጣው አሊ ኢብን ዳውድ ከሚባለው እንደ አው. ቀ.
በ፲፮፻፵፯ - ፲፯፻፵፰ ዓ. ም. ላይ ሐረርን ከሚያስተዳድረው ነው ። የሁለቱም የማዕ
ርግ ሥያሜ አሚር ስለሆነ ምናልባት ከላይ ከኑር ኢብን ሙጃሂድ የመጣ ዘር ይኖ
ራቸው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ በሰሜን የኢጣልያ መንግሥት ቀደም ብሎ አሰብን እንደ አው. ቀ.
በ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ምጥዋን በ፲፰፻፸፭ ዓ. ም. ከያዘ ወዲህ ሐረርጌንም ለመያዝ
በመመኘት ሰላይና አገር መርማሪ በኮንቴ ፖሮ (CONTE PORRO) መሪነት ልኮ
ሳለ ገረስሌ አጠገብ ሐርቲ ከሚባለው ቦታ ሲደርስ ነገሩ የገባቸው የአሚር አብዱ
ላሂ ሰዎች ሁሉንም ፈጅዋቸው ። በዚህ ጊዜ የኢጣልያ መንግሥት ዜጋዎቼ እነ
ፖሮ ከተገደሉ የሟቾቹን ዜጐቼን ደም ተበቅዬ ወዲያውም አገሩን ሐረርጌን እይ
ዛለሁ እያለ ጥላንና ጊዜ ሲያማርጥ ንጉሥ ምኒልክ አስቀድመው ያዙት ። ሲይዙ
ትም ነገሩ በአውሮፓዎችና በኢጣልያም ዘንድ ከፍ ያለ ግጭት እንዳይፈጥር በበኩ
ላቸው ፈረንሳዊና እንግሊዝም ይኸንኑ ሐረርጌን በቅርብ ጊዜ ከያዙት ቅኝ አገራ
ቸው ጋር ለመደባለቅ ምኞት ስለነበራቸው ምኒልክ በተለመደ የፖለቲካ ዘዴያ
ISIC
ቸው በልስላሴ መንገዱን ለመደልደል ማሰባቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ለኢጣ
ልያ ንጉሥ የጻፉት ረዘም ያለ ደብዳቤ ያስረዳል ።
በደብዳቤው ውስጥ ሌላም ጉዳይ ስላለ ሁሉን ማስፈር ስለሚረዝም ሐረርጌን
ለመያዝ ያላቸውን ምኞት የሚጠቅሰውን እየመረጥን ከዚህ እንደሚከተለው በዚ
ያው በደብዳቤው አጻጻፍ እንዳለ አስፍረንዋል ።

«የተላከ ከንጉሥ ምኒልክ ይድረስ ከከበረ ከታፈረ የኢጣልያ ንጉሥ ዓምበር
(ኡምቤርቶ) . . . . . . ንጉሥ ሆይ . . . . . . አሁን እምነግርዎ ነገር እጅግ የከበደ
የበረታ ነገር ነው ። በዚህ ደብዳቤ ቃል ፍቅሬንና ማክበሬን እንዲያውቁልኝ ተስፋ
አለኝ ። ይህ ደብዳቤ ሲደርስ ሐረርጌንና የሐረርጌን አውራጃ አገር ሁሉ መያዜን
ጥርጣሬ የለውምና ያውቁት ብዬ ነው ። ይህም አገር በእያቴና በቅድመ እያቴ
ዠምሮ የሸዋ ግዛት ነበር (1) ። በዚህ ነገር የተነሣ የአውሮፓ ሰዎች የሚሉትን አላ
ውቅም ። ይከፋ አይመስለኝም ። አሁን ንጉሥ የሚገባኝን ገንዘቤን አገሬን ነውና
የወሰድሁት ስለኔ ሆነው ለዚህ ነገር የሚነሣውን ሁሉ ይመክቱልኝ ብዬ እለምንዎ
ታለሁ ።

ዳግመኛም ይህን አገር የያዝሁበት ምክንያት ባጭሩ አስረዳዎታለሁ ። ሐረርጌ
ቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ሳለ የአገሬ ጭማሪ ነበር ። የእስላሞች ጦርነት የተ

(1) በእያቴና በቅድም እያቴ ሲሉ በነዘርዓ ያዕቆብ ፣ በነ ልብነ ድንግል ማለታቸው እንጂ በወሰን
ስገድና በሣህለ ሥላሴ ጊዜ ማለታቸው እንደማይሆን ዕውቅ ነው ።

ነሣ ጊዜ ከሁሉ ይልቅ የግራኝ ጦርነት ኢትዮጵያን ያጠፋ ጌታ በተወለደ በ፲፮፻ ዘመን ብዙ አገር ሄደብን ። ከሄደብን አገር ሁሉ ቍጥር አንዱ ሐረርጌ ነው ። እግዚ አብሔር ግን ክርስቲያንን አይጥልምና እኛ በጉልበታችንም ሆነ እውነትንም ይዘን ሆነ እስላሞች ያጠፉብንን አገር ሁሉ እየተዋጋን እንደገና እያቀናን መለስነው ።

የእስጣንቡል መንግሥትና የምስር መንግሥት ያባቶቻችን መንግሥት ጥፋት አገዛቸውና በባሕር ዳር የነበረውን አገራችንን ሁሉ ሐረርጌን ጨምረው ይዘውብን ነበር ። ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ በእግዚአብሔር ኃይል ቱርኮችን ድል አድርገው ኢትዮጵያን አተረፉት . . . . . እኛ ግን እርቅን ሰላምን እንወዳለን ዳግመኛ ጦር ነቱን ብንጠላው ቱርኮች ሐረርጌ ላይ ቢቀመጡ ዝም ብለናቸው ነበር ። አሁን ግን ነገሩ ተለዋወጠ ። ሐረርጌ ላይ ያሉት ወዳጆቼ ከ፮ ወር ዠምረው አገሩ በጋሎች እጅ ሆነ ከዚያ ያለ ሰው ሁሉ ፈርቷል እያሉ ዕለት ዕለት ይጽፉልኛል ። አሁን እን ኳን በመጨረሻ የመጣው ደብዳቤ ቱርኮች ጨርሰው ለቀቁት የሚል ነው . . . . . ያያቶቼን መንግሥት የእስላም ሽፍታ ወጥቶ እንዳጠፋው ዳግመኛ የእስላም ሽፍታ ወጥቶ በኔ መንግሥት ይጫወትበት ብዬ ዝም ብዬ አላይም . . . . . ሐረርጌ ስንገባ ሰውን ሁሉ በሃይማኖቱ እናኖራለን ። ሀብታሙንም ደሀውንም እኩል እንገዛለን ፤ እንጠብቃለን ፤ ንግድም እንዲቀና በጣም እንጥራለን . . . . . . ይህ መልካሙ ሐሳ ባችን በንጉሥ ፊት የተወደደ እንዲሆንልን ተስፋ አለን ። ሁሉን የሚችል እግዚአ ብሐር ንጉሥንም ሕዝብዎንም መንግሥትዎንም እንዲጠብቅ እለምናለሁ (1) ።»

ደብዳቤው የተጻፈው በግንቦት መሆኑን ሲያመለክት ዓመተ ምሕረቱ እንደሌላ ዎቹ አልተጻፈበትም ። ነገር ግን ዓመተ ምሕረቱ እንደ ኢት. ቀ. ፲፰፻፸፰ ዓ.ም. መሆን አለበት ።

ስለዚህ በግንቦት ወር ፲፰፻፸፰ ዓ. ም. ይኸን ደብዳቤ ጽፈው በስምንተኛው ወር በታኅሣሥ ፲፰፻፸፱ ዓ. ም. ወደ ሐረርጌ ዘምተው በታኅሣሥ ፳፱ ቀን የትን ግሌ ለት አሚር አብዱላሂን ጨለንቆ ላይ ወግተው በማሸነፍ ሐረርጌን ይዘ ዋል (2) ። የኢጣልያ ንጉሥ ለጻፉለት ደብዳቤ መልስ አልሰጣቸውም ። እርሳቸ ውም የጻፉት እንዲያውቀውና ቢቻል በነገሩ እንዳያዝንበት ለማድረግ ይሆናል እንጂ መልስ የጠበቁ አይመስልም ።

ከዚህ በፊት እንዳልነው ዓፄ ምኒልክም በደብዳቤያቸው እንዳሉት ሐረርጌ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር መሆኑ በውስጡ የእስላም ባላባቶች ቢፈራረቁበትም ባላባ

(1) ኢኛሲዮ ጉዲ I due Framenti Relativi alla Storia di Abissinia. በሚል አርእስት ካሳተመው ውስጥ ።
(2) ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ን. ነ. ዘኢት. ገጽ 144 - 145 ፤

የግራኝ አህመድ ወረራ

ቶቹ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሥር እንደነበሩ ጥርጥር የለውም (1) ።
ነገር ግን በግራኝ አህመድ የወረራ ዋዜማ በይፋት የነበሩት የወላስማ ባላባቶች
ከጥንቱ የትውልድ አገራቸው ከዓረብ አገር መጣሪያ እያገኙ እያደር ኃይል ስለተሰ
ማቸው በአቡበከር ኢብን መሐመድ ጊዜ ከነበሩበት ከይፋት ቀጥሎ ከአዳል ከተማ
ቸው ከዳካር ተዛውረው በ፲፭፻፲፪ ዓ. ም. ወደ ሐረር መጥተው ተቀመጡ (2) ።
ወዲያው የግራኝ አህመድና የሱልጣኖቹ ጦር ከዙሪያው በመሰብሰብ ሐረር ላይ
እየተጠራቀመና እየተደራጀ ያው ባለፉት ምዕራፎች እንደተነበበው ከሐረር ከተማ
እየተነሣ ያዒ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለመገልበጥ ቻለ ። ግራኝ አህመድ ከሐረ
ርጌ እየተነሣ ወደ ደዋሮ ወደ ፈጠጋር ወደ ባሌ ወደ ቤተ አምሐራ በመዝመት
ዘምቶ የገደለውን ገድሎ ያሰለመውን አስልሞ የዘረፈውን ዘርፎ ተመልሶ የሚያር
ፈው ሐረርጌ ነበር ። በጦርነቱ ሰዓት ፩ ጊዜ ያህል በመመላለስ ለግራኝ አህመድ
ሐረር መነሻ ተመልሶ ማረፊያውና መድረሻው እንደነበረ ባለፈው ያነበብነው
ሁሉ በሰፊው አስረድቶናል ። ወደ ሐረር መመለስን የተወው ስሚን ኢትዮጵያን
በወረራ አዳርሶ ገዥነት ሲሰማው ለመቀመጫ ደንቢያን የመረጠና እርሱና ሹማም
ንቱ ጓዛቸውን ካስመጡ በኋላ ብቻ ነው ።

ከግራኝ በኋላ የርሱና የኑር ተወላጆች ይማምና ኤሚር እየተባሉ በሐረር
ግዛት ከተፈራረቁበትና የግብፅ ገዥነት አሥር ዓመታት እነርሱ የሾሙት ኤሚር
አብዱላሂ ሁለት ዓመታት ከገዙ በኋላ እንግሊዝና ፈረንሳዊም ይዘው በቅርብ ካላ
ቸው ቅኝ አገር ለመደባለቅ ሲያደቡ ፤ በእንግሊዝ የተደገፈ፲፰፻፸ኢጣልያ መንግሥት
እንደምጥዋና እንዳካባቢው ግብጾች በሚለቁት መተካትን እንደ አንድ ደንበኛ
መብት በመቁጠር ለመያዝ በሚመኝበት ሰዓት ዳግማዊ ምኒልክ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም.
ያዙት ።

ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወታቸው ለኢትዮጵያ ከሠሩዋቸው ታላላቅ ውለታዎች
ውስጥ ሐረርጌን ከአሚር አብዱላሂ እጅ መውሰዳቸው ብቻ ሳይሆን ከኃያላኑ መን
ግሥታት ቀድመው መያዛቸው አንደኛውን ከፍተኛ ቦታ መያዝ አለበት ። በዚያን
ጊዜ እርሳቸው ችላ ብለው ወይም የኃያላኑን መንግሥታት ጠብ በሩቁ በመ
ፍራት ከኢጣልያም ላለመጣላት ሲሉ ሐረርጌን ባይዙ ኑሮ የኢጣልያ ሐረርጌን
መያዝና የኢጣልያ ሱማሌ ይባል ከነበረው ከቅኝ ግዛቱ ጋር መደባለቁ የማይቀር

ሐዬ የሚባለው የሐበሻ ንጉሥ በየዓመቱ ከማ
(1) አል ማከሪዚ የሚባለው የዓረብ ጸሐፊ «. . . . . . ያስገብራል ፤ በውስጡ 99 መንግሥታት አሉት ከነዚሁ
ናቸውም ሀብት ከሥር አንድ (አሥራት) ናቸው» ይላል ። በማከሪዚ መጽሐፍ እስላም የትናንትና የዛሬው
ሰባቱ የእስላም ነገሥታት የጻፈው ገጽ 299 ፤
በሚል እርእስት ቼሩሊ የጻፈው ገጽ 299 ፤
(2) ዳካር ከሐረር በምሥራቅ በዙል በአዳል ውስጥ ፊደምቢሮ አጠገብ ።

ስለነበረ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ የእንግሊዝና የኢጣልያ ሱማሌ የተባ ሉት በኅብረት የመንግሥት አቅዋም ሲያገኙ የሐረርጌ እድል እምን ውዝግብ ላይ ያርፍ ነበር ብሎ ለማሰብ ቀላል ነው ። ስለዚህ የኋለኛው ውዝግብ ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. የልደት ለት ጨለንቆ ላይ በቅድሚያ ተወገደ ማለት ነው ። ውግዲቱን አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የማድረጉ ተግባር ያሁኑና የሚመጣው ትውልድ ፋንታ ነው ።

ጥንት እነዓፄ ዓምደ ጽዮን እነዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነበሩበት በግራኝ ወረራ ዋዜማ እነ አባ ገብረ እንድርያስ እነራስ ደገልሃን ከግራኝ ወረራ ፍጻሜ በኋላ እነ እዝማች ፋኑኤል እነ አቤቶ ሐመልማል የተጋደሉባት ሐረር አሁን በመጨረሻ ዓፄ ምኒልክ ከያዙት ወዲህ ልዑል ራስ መኰንን ከመኳንንቶቻቸው ጋር ከሸዋውና ከቤገምድሩ ከጐጃሜውና ከትግሬው ከጋላው ተወላጅ ጋር ለዚህ ምድር የአእምሮና የጉልበት ኃይላቸውን አፍሰውበታል ። የነዚህ የትክለኞቹ ተወላጆች ዛሬ በሕይወት የሚገኙት አገሬ ሸዋ ነው ቤገምድሬ ነኝ ጐጃሜና ትግሬ ነኝ በማለት ፈንታ የሐረር ተወላጅ ነኝ ይላሉ ። ከሀገሬው ተወላጅ ከአደሬው ከሱማሌው ከጋላውና ከኢሳው ከአዳሉ ጋር ዘራቸውን ለማዳቸውን ደባልቀው ይኖሩበታል ። ስለዚህ እንደሌላው እውራጃ በሐረርጌ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነው ሁሉ አገሪቱን ለመጠበቅ የግዴታ ኀላፊነት እንዳለበት ባገሪቱም እየተጠቀመ ለመኖር ሙሉ መብት አለው ።

ተፈጸመ ።

መጽሐፉ ፯ ክፍሎች ፻፶፭ ምዕራፎች ፰፻፺ ገጾች እስኪወጣው ድረስ የሰነድ ስብሰባው ግዕዝኛውን በቀጥታ የፖርቱጋልኛውንና የአረብኛውን ሰነድ እያነጣጠሩ የማሳካቱ ተግባር ከሁሉ የበለጠ እነዚህን አንተርሶ እያዛመዱ በጽሑፍ የማስፈሩና የማሳተሙ ጉዳይ ረዘም ያለ ጊዜ ወስዷል ። በሥራና በመዝናናት መካከል ጊዜ እያጠረ ከዚህ የበለጠ የማስበውን ያህል በተጣራና በጥሩ ያነጋገር ወዝ በመቀመም ደንበኛ የሥነ ጽሑፍ ደረጃ ለመስጠት ካለመቻሌ በላይ ከሥር እያያያዙ ለማብራራት በመፈለግ ብዙ ቃላትና የሰነድ ጥቅሶች እንደተደጋገሙ ይሰማኛል ። እንደዚሁም በኋላ የተገኙ ፯ ሰነዶች ገጽ አልተሰጣቸውም ። ስለዚህ ከዚህ ካሁኑ የተሻለው አቀራረብ ከጡረታ ጊዜና ከዕድሜ ሊወለድ የሚችለውን ሁለተኛ እትማት ይጠብቅ ። ላሁኑ መጽሐፍ የረዱኝን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ ።

ተ. ጸ. መ.

# የስም ፤ የአገርና የቦታ ዝርዝር

ISIC

ISIC

# የስም ዝርዝር

...ሀ...


ሀብተ ጊዮርጊስ (ፊታውራሪ) ፡ ፹፰ ፡ ፻፴፪ . . . ብዙ ጊዜ
ሀመበስ (ሀውባስ) ፡ ፰
ሂሚያሪት ፡ ፯
ሂራቡ (የሱማሌ ባላባት) ፡ ፪፻፶፬ ፡ ፪፻፶፯ ፡ ፪፻፶፯ . . . ብዙ ጊዜ
ሂትለር ፡ ፪፻፹፰ ፡ ፪፻፹፱ ፡ ፯፻፱ . . . ብዙ ጊዜ
ሂፖክራት ፡ ፶፯
ሂክቶር ዶ. ሲልቬይራ ፡ ፰፻፳፯
ሃይቢ (ሐይቢ ሐይብ አዝማች) ፡ ፪፻፳፯ ፡ ፪፻፵ ፡ ፫፻፲፫ ፡ ፰፻፫ . . . ብዙ ጊዜ
ኃይሉ ቡባሞ ፬፻፴


...ለ...


ሉቃስ (ወንጌላዊ) ፡ ፳፰ ፡
ሉተር (ማርቲን) ፡ ፻፰ ፡ ፫፻፴፬
ሉዊዝ ዶ. ሜኔዚስ ፡ ፻፶፩
ሉዊዝ ሮድሪጌዝ ዳ. ክርቫልሆ ፡ ፮፻፶
ሉዊ ፲፮ኛ ፡ ፰፻፹፫
ሊትማን (ኢኖ) ፡ ፩ ፡ ፮፻፴፩ ፡ ፯፻፳፬ ፡ . . . . . . . ብዙ ጊዜ
ላሊበላ (ቅዱስ ወይም ቤተ ክርስቲያን) ፡ ፴፪ ፡ ፸፱ ፡ ፹፳ ፡ ፯ ፡ ፰፻፳፪ . . ብዙ ጊዜ
ላክሮዝ ፡ ፰፻፳፩ ፡ ፯፻፳፬ . . . ብዙ ጊዜ
ላዛሮ ዶ አንድራዶ ፡ ፻፶
ሌዊ ፡ ፰፻፴፰
ሌዋኒዳ ፡ ፶፯
ልብነ ድንግል ፡ ፬ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ፡ ፵፫ ፡ ፵፰ ፡ . . . ብዙ ጊዜ
ልዮን ፲ኛ (የሮማ ሊቀ ጳጳስ) ፡ ፻፯ ፡
ሎፖ ዲ. አልማንዛ ፡ ፮፻፹፩
ሎፖ ስዋርስ (ሎፖ ሱአሬስ ፣ ዮአሬስ) ፡ ፻፬ ፡ ፰፻፳ ፡ . . . . . ብዙ ጊዜ


...ሐ...


ሐመልማል (አቤቶ) ፰፻፲፬ ፡ ፰፻፲፰ ፡ ፰፻፵፩ ፡ . . . ብዙ ጊዜ
ሐሙራቢ ፡ ንጉሠ ባቢሎን ፡ ፰፻፴፰
ሐቀዲን (ሐቅ አድ ዲን) ፡ ፲፯ ፡ ፸፬ ፡ ፻፸፫ . . . ብዙ ጊዜ
ሐና (የላሊበላ ገዥ) ፡ ፫፻፳፫
ሐንሪ (የቡርጎኝ ዘር) ፡ ፶፯
ሐዋርያ ክርስቶስ (አዛዥ) ፡ ፲፬ ፡


ISIC

ሐጂራህ (ቀድሞ የአዝማች ተክለ ሃይማኖት ሚስት በኋላ ግራኝ የመለያላት)
፻፰፰ ፣ ፻፰፰ ፣ ፻፰፴፰ ፣ . . . ብዙ ጊዜ
ሕንሪ ፬ኛ (የእንግሊዝ ንጉሥ) ፹፱
ሕንሪ ፭ኛ ፯፻፶፬
ሕንደኬ ንግሥት ፣ ፹፭
ሐሜር ፣ ፭፯ ፣ ፴፯ ፣ . . . ብዙ ጊዜ


...መ...


መሐመድ (ነቢዩ) ፣ ፶፭ ፣ ፻፩ ፣ ፯፻፸፯ ፣ ፰፻፴፩ . . . ብዙ ጊዜ
መሐመድ ቤን አህመድ (ሼህ) ፻፸፱
መሐመድ (ሱልጣን) ፣ ፻፰፩
መሐመድ ፪ኛ ፶፯
መሐመድ ቤን በድላይ (ዓርዌ በድላይ) ፣ ፶፯ ፣ ፶፱ ፣ ፩፻፴፩ . . . ብዙ ጊዜ
መሐመድ ኢብድን አዝሃር ኢዲን ፣ ፻፱
መሐመድ (ዘሐድያ) ፻፴
መሐመድ (የደዋሮ ባላባት) ፣ ፻፴
መስቀል ክብራ ፣ ፸፱
መከትር (ሱልጣን መከተር የመዘጋ ባላባት) ፣ ፩፻፹፭ ፣ ፩፻፹፱
መዓዛ ለማ ፣ ፶፭
ሙራድ ካሚል ፯፻፯
ሙራድ ፣ ፶፯
ሙሴ (እስራኤላዊ ዕብራይስጥ ሞሼ) ፣ ፲፭ ፣ ፳፬ ፣ ፴፱ ፣ ፴፯ ፣ ፫፻፴፱ . . . ብዙ ጊዜ
ሙሶሊኒ ፬፻፸፯ ፣ ፯፻፳፭ ፣ ፯፻፲ . . . ብዙ ጊዜ
ሙኒማህ (የግራኝ እህት) ፣ ፱፻፭ ፣ ፱፻፯ ፣ ፱፻፳ . . . ብዙ ጊዜ
ሙጃሂድ (ወዚር) ፣ ፫፻ ፶፭ ፣ ፬፻፶፩ ፣ ፬፻፶፱ ፣ ፬፻፹፬ ፣ . . . ብዙ ጊዜ
ሚልክያስ (ነቢይ) ፣ ፳፬
ሚሸል አንዥ ፣ ፴
ሚናስ (አቤቶ) ፣ ፻፸፯ ፣ ፯፻፶፳ ፣ ፯፻፹፱ . . . ብዙ ጊዜ
ሚናስ (ዓፄ) ፣ ፸፳ ፣ ፹፱ ፣ ፹፬ ፣ ፻፴፩ ፣ ፻ ፶፱ ፣ ፭፻፸ . . . ብዙ ጊዜ
ሚካኤል (ኤጲስ ቆጶስ) ፣ ፳፯
ሚካኤል ግብፃዊ ፣ ፻፲፯
ሚጉኤል ዴ. ካስታንሆዞ ፣ ፴ ፣ ፯፻፯ ፣ ፯፻፱ ፣ ፯፻፱ ፣ ፯፻፳፳ ፣ ፯፻ ፣ ፯፻፳ . . . ብዙ ጊዜ
ማሊክ ሳሊህ ፣ ፶፯
ማሕረም (ማኅረም መሕርም) ፣ ፲፱ ፣
ማመሉክ ፣ ፶፱ ፣ ፶፯ ፣ ፶፰ ፣ . . . . . . . . ብዙ ጊዜ
ማርቆስ (ወንጌላዊ) ፳፭ ፣ ፳፰ ፣ . . . . ብዙ ጊዜ

ማርቆስ (አቡነ ጳጳስ)፤ ፴፩፤ ፶፤ ፷፰፤ ፸፩፤ ፸፯፤ ፻፳፯፤ ፻፴፯፤ ፻፴፰፤ ፻፷፬፤
፻፲፯ ... ብዙ ጊዜ
ማንሱር (ገሪድ)፤ ፻፲፯
ማታን (ገሪድ) ፻፴፩፤ ፻፺፬፤ ፬፻፬፤ ፬፻፯፤ ፬፻፲ ... ብዙ ጊዜ
ማቴዎስ (አርመናዊ፤ አብርሃም)፤ ፺፰፤ ፷፷፤ ፷፱፤ ፻፯፤ ፻፲፫፤ ... ብዙ ጊዜ
ማቴዎስ (ወንጌላዊ)፤ ፳፩፤ ፷፷፤ .... ብዙ ጊዜ
ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል (ብ. ጌታ)፤ ፫፻፸፪
ማኅፀንቶ (ራስ ሕዱግ)፤ ፻፳፱፤ ፻፴፯፤ ፳፻፳፤ .... ብዙ ጊዜ
ማኅቶዝ (ማኅቶድ)፤ ፸፯፤ ፺፯፤ ፺፷፤ ፺፱፤ .... ብዙ ጊዜ
ማኑኤል ዳ. ኩንሃ፤ ፪፻፷፱
ማክሪዝ፤ (አልማክሪዚ)፤ ፲፩፤ ፵፤ ፵፬፤ ፻፤ ... ብዙ ጊዜ
ማክዳ (ንግሥት)፤ ፬፻፸፬
ሜንዴዝ፤ ፭፻፺፯
ምኒልክ (ቀዳማዊ የሰሎሞን ልጅ)፤ ፲፩፤ ፲፪፤ ፲፯፤ ፴፪፤ ፴፯፤ ... ብዙ ጊዜ
ምኒልክ (ዳግማዊ ዓፄ)፤ ፲፤ ፲፬፤ ፳፯፤ ፴፯፤ ፵፯፤ ፶፤ ፶፩፤ ፶፪፤ ፶፫፤ ብዙ ጊዜ
ምንትዋብ (እቴጌ)፤ ፻፴፩፤ ፳፻፺፬ ... ብዙ ጊዜ
ሞሪዮ ዣን (ዶራሲ)፤ ፻፷፪
ሞንተስኪዩ (ፈረንሳዊ)፤ ፲፱

ISIC

...ሠ...

ሠርጤ (ሠርጌ) ቢትወደድ፤ ፺፬፤ ፻፲፪፤ ፻፲፫፤ ፻፲፬፤ ፬፻፺፬ ... ብዙ ጊዜ
ሠርፀ ድንግል (ዐፄ)፤ ፲፰፤ ፴፯፤ ፴፰፤ ፸፬፤ .... ብዙ ጊዜ
ሠርፀ ድንግል (ዘዳሞ)፤ ፳፻፴
ሠይፈ አርዕድ (ዓፄ)፤ ፱፤ ፴፰፤ ፶፤ ፻፸፱ ... ብዙ ጊዜ
ሣህለ ሥላሴ (የሸዋ ንጉሥ)፤ ፸፳፤ ፬፸፫፤ .... ብዙ ጊዜ
ሥርግው ሀብለ ሥላሴ (ዶክተር)፤ ፻፺፬

...ረ...

ረኔ ለፌቨር፤ ፳፻፳፩
ረኔ ባሴት (ሙሴ)፤ ፻፬፤ ፻፷፷፤ ፻፷፱፤ ፬፻፺፱ ... ብዙ ጊዜ
ራማ (የሕንድ ንጉሥ)፤ ፩
ራትኤል (መልአክ)፤ ፸፪
ሩፋኤል፤ ፴
ሮማን ወርቅ፤ ፯፻፸፱፤ ፻፲፬፤ ፻፲፰ ... ብዙ ጊዜ

ሮቤል (ጸሐፊ ላም) ፪፻፲፰ ፤ ፪፻፳፬ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ሮድሪግ ጎንዛሎ ፤ ፯፻፰፬ ፤ ፯፻፸፫ ፤ ፯፻፸፯ ፤ ፯፻፹፰ ፤ ፰፻፲፯ . . . . ብዙ ጊዜ
ሮደሪግ ደ. ሊማ (ዶም ሮደሪግ) ፤ ፵፰ ፤ ፻፳፬ ፤ ፻፳፮ ፤ ፻፴፪ ፤ ፻፴፬ ፤ ፻፵፩ ፤ ፻፶፱ . . .
ብዙ ጊዜ

...ሰ...

ሰሊም ፩ኛ (የቱርክ ሱልጣን) ፤ ፯፻ ፺፬
ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (አባ ፤ ጳጳስ) ፤ ፫፻፸፩
ሰሎሞን (የእስራኤል ንጉሥ) ፤ ፲፪ ፤ ፲፫ ፤ ፲፭ ፤ ፲፯ ፤ ፴፪ ፤ ፴፯ ፤ ፵፭ ፤ ፩፻፴፯ ፤ . . .
ብዙ ጊዜ
ሰበነ ጊዮርጊስ ፤ ፹፪
ሰብለ ወንጌል (እቴጌ) ፤ ፶ ፤ ፸፰ ፤ ፸፱ ፤ ፻፳፩ ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፴፪ ፤ ፩፻፰፪ . . . ብዙ ጊዜ
ሰብረዲን (ሳብር ዓድ ዲን) ፴፪ ፤ ፻፸፩ ፤ ፬፻፳፩ ፤ . . . . . . . ብዙ ጊዜ
ሰዓዲን (መሐመድ አቡል በረከት ሰአድ አድ ዲን) ፬፻፹፩ ፤ ፳፻፳፮ ፤ . . ብዙ ጊዜ
ሰፒኖዛ ፤ ፳፰
ሲሴሮ ፤ . . . ፶፯
ሱስንዮስ (ዓፄ) ፲ ፤ ፲፱ ፤ ፬፻፳፰ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ሲልቬይራ . . . ፭፻ ፶፭
ሲዲ ሞሐመድ ሀንዱል ፤ ፫፻፹፯ ፤ ፬፻፹፯ . . . ብዙ ጊዜ
ሲዲቅ (ገራድ ሻርቃህ) ፬፻፶፩ ፤ ፬፻ ፶፰ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ሲዲ ኡክ ሸረፍ አብዱራህማን ፤ . . . . ፭፻፪
ሲድ መሐመድ ፤ ፮፻፸፫ ፤ ፮፻፰፬ ፤ ፮፻፳፭ ፤ ፮፻፹፫ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ሳሊም ፤ ፻፲፪
ሳላህዲን (ሱልጣን) ፤ ፹፭
ሳሙኤል (የእስራኤል መስፍን) ፳፬
ሳሙኤል አባ (ዘደብረ ዓባይ) ፤ ፬፻፹፩
ሳሙኤል አባ (ዘቋየጻ) ፤ ፬፻፹ ፤ ፬፻፹፩
ሳባ (የዮቅጣን ልጅ) ፤ . . . . ፯
ሳባ (ንግሥት) ፤ ፩ ፤ ፯ ፤ ፲፩ ፤ ፲፯ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ሰባጋዲስ (ደጃዝማች) ፤ ፻፳፱
ሳዖል (የእስራኤል ንጉሥ) ፤ ፳፬
ሳዶቅ (ካህን) ፤ ፬፻፸፱
ሳፍ ሰገድ (ሳፋ) በ፬፻፳፯ እና ፬፻፳፯ መካከል
ሴም ፤ ፯
ሴኔክ . . . ፶፯
ስታንሌይ (ሎርድ) . . . ፻፵፪
ISIC

ስሑል ሚካኤል (ራስ) ፪፻፵ ፣ ፫፻፴ ፣
ሶለይማን (ሶሊማን ሱልጣን) ፶፮ ፣ ፶፯ ፣ ፪፻፲፪ ፣ .... ብዙ ጊዜ
ሶሌይማን አህመድ .... ፻ ፣ ፻፵፫ ፣ ፫፻፴፭ ፣ ... ብዙ ጊዜ
ሶሎን ፣ ፶፫
ሶክራት ፣ ፹፮ ፣ ፶፫ ፣

...ሸ...

ሺሃብ ኤዲን አሕመድ ቤን አብድር ቃድር (አረብ ፋቂሀ) ፣ ፵ ፣ ፻፷፰ ፣ ፻፹፫ ፣
፭፻፹፮ ፣ ...... ብዙ ጊዜ
ሸመን (ገራድ ስምዖን) ፪፻፴፮ ፣ ፫፻፹፮ ፣ ፬፻ ፶፰ ፣ .... ብዙ ጊዜ
ሺምሺያ (የግራኝ እናት ?) ፣ ፻፷፮
ሸምስ አድ ዲን መሐመድ ፣ ፻ ፶፬
ሸምሱ (ሱተለይ) ፣ ፫፻፲ ፣ ፫፻፵ ፣ .... ብዙ ጊዜ
ሸርል ሯኛ (የጀርመንና የእስፓኝ ንጉሥ) ፣ ፻፷
ሸንባል በአልዊ ፣ .... ፵፮
ሸውል (አገባች) ፭፻ ፶፭

...ቀ...

ቀሊምንጦስ ፯ኛ (የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት) ፣ ፲፫ ፣ ፻፶፪ ፣ ፻፶፬ ፣ ፭፻፷ ፣ ፭፻፶ ፣
ISIC
... ብዙ ጊዜ
ቂሮስ (የፋርስ ንጉሥ) ፹፬ ፣ ፭፻፴፫
ቄርሎስ (አቡነ) ፲፫ ፣ ፴፮ ፣ .... ብዙ ጊዜ
ቄርሎስ አባ (የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት) ፪ ፣ ፹፮
ቆስጠንጢኖስ (ትልቁ) ፣ ፴፪

...በ...

በረላዓም .... ፻፲፰
በረይተማ ... ፲
በሻህ (አቶ) ፻፶፬
በካፋ (ዓፄ) ፲ ፣ ፻፴፭
በዕደ ማርያም (ዓፄ) ፱ ፣ ፲፫ ፣ ፴፪ ፣ ፴፫ ፣ ፸፪ ፣ ፸፫ ፣ ፹፮ ፣ ፺ ፣ ፺፭ ፣ .... ብዙ ጊዜ
በድላይ (በድሌ ቢትወደድ) ፣ ፪፻፹፫ ፣ ፪፻፺፭ ፣ ፪፻፺፮ ፣ .... ብዙ ጊዜ
በድላይ ሺሀብ አድ ዲን አህመድ (አርዌ በድላይ) ፣ ፻ ፣ ፪፻፺፭ ፣ ..... ብዙ ጊዜ
ቡላ (የባሕር ነጋሽ ዶሪ ልጅ) ፣ ፪፻፵፪
ቪርጆል .... ፶፮

ባሕርይ (አባ) ፰፻፱ ፤ ፰፻፰ ፤ . . . . . ብዙ ጊዜ
ባርሰቤይ (ሱልጣን) ፤ . . . ፯
ባርተን ፤ ፻፸፩
ቫስኮ ዳጋማ ፶፱ ፤ ፮፻፸፯ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ባቅላ ፤ ፶፰
ባኑ ሐሴም ፤ ፻፸፰
ባኑ አብድአል አዳር ፤ ፻፸፰
ቤርሙዴዝ (ዮሐንስ) ፵፩ ፤ ፵፱ ፤ ፶ ፤ ፶፩ ፤ ፶፰ ፤ ፻፶ ፤ ፻፶፩ ፤ ፮፻፹፱ ፤ ፯፻፫ ፤ ፯፻፵ ፤
፱፻፱ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ብሩቱስ ፤ ፰
ብራንካ ሌዎን ፤ ፻፴፯ ፤ ፻፴፱ ፤ ፻፵፱ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ብእሴ እግዚአብሔር ፤ ፩፻ ፶፰

... ተ ...

ተስፋ ልዑል (እቃጽን ሠራዊ) ፤ ፩፻፰፯ ፤ ፩፻ ፶ ፤ ፩፻ ፶፰ ፤ ፩፻ ፶፱ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ተስፋ ኢየሱስ (የባሕር አምባ ገዥ) ፤ ፱
ተክለ ሃይማኖት (አገዛማች) ፤ ፻፴፩
ተክለ ሃይማኖት ወልደ ኪዳን (ቄስ ገበዝ) ፤ ፻፶፩
ተክለ ሥላሴ (አዛዥ ጤኖ) ፲፱
ተክለ ኢየሱስ (አዝማች ወይም ትግሬ መኰንን) ፱ ፤ ፩፻ ፶፩ ፤ ፫፻፩ ፤ ፩፻፸ ፤ ፰፻፰ ፤
. . . . ብዙ ጊዜ
ተክለ ጊዮርጊስ (ዓፄ) ፍቅር ሰገድ ፤ ፵፯
ተክለ ጊዮርጊስ (አዝማች) ፰፻፸፰ ፤ ፰፻፸፯ ፤ . . . ብዙ ጊዜ
ቱማን (ሱልጣን) ፤ ፶፰ ፤ ፻፴፩ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ቱማን ቤይ ፤ ፶፱ ፤ ፻፰ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ታክለ ወ. ሐ. (ብላታ ደጃዝማች) ፩፻፵፩
ታየድራ . . . . ፹፱
ታዬ (አለቃ) ፯
ታዴዎስ (ዘባልታርዋ) ፤ ፰፻፹፱
ቴዎድሮስ (ዓፄ አባ ታጠቅ) ፤ ፩፻ ፶፱ ፤ ፰፻፹፫ ፤ . . . . . ብዙ ጊዜ
ቴዎድሮስ (ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ) ፤ ፰
ቴዎድሮስ (አቤቶ) ፰፻፹፯ ፤ ፰፻፹፰ ፤ ፰፻፹፱ ፤ ፰፻፴ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ቴዎዶስዮስ ዳግማዊ ፤ ፴፫
ትሪስታን ዳ. ኩኛ (የጦር አለቃ) ፤ ፸፰ ፤ ፸ ፤ ፻፶፱ ፤ . . . . ብዙ ጊዜ
ቶማስ ዳኪን . . . . ፴፯

ISIC

...ቸ...

ቼሩሊ (አንሪኮ) ፹፱ ፡ ፺፭ ፡ ፺፬ ፡ ፯፻፹፫ ፡ ፰፻፳፯ ፡ ፰፻፴፫ ፡ ፰፻፴፱ ... ብዙ ጊዜ

...ኀ...

ኃራማደይ ፡ ፺፬
ኃይለ መለኮት (ንጉሥ) ፡ ፬፻፫
ኃይለ ማርያም ማሞ ፡ ፬፻፵፭
ኃይለ ሥላሴ (ቀዳማዊ ዓፄ) ፡ ፲፪ ፡ ፬፻፸፫ ፡ ፬፻፹፫ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
ኃይሉ (ታላቅ ራስ ኃይሉ) ፡ ፹፭
ኃይሉ እሸቴ (ደጃች) ፡ ፬፻ ፺፪
ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) ፡ ፺

...ነ...

ነስረዲን ፲፯ ፡ ፺፯ ፡ ፭፻ ፺፭ ፡ ፯፻፵፱ ፡ ፯፻፵ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
ነቢያት (ራስ) ፡ ፱፻፵፫ ፡ ፱፻፵፯ ፡ ፱፻፵፯ ፡ ፱፻፸፱ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ነአኵቶ ለአብ (ዓፄ) ፡ ፺ ፡ ፪፻፹፱ ፡ ....... ብዙ ጊዜ
ነገደ ኢየሱስ (ዓቃቤ ሰዓት) ፡ ፬፻ ፺፯
ኑር (ሸሪፍ) ፭፻፪ ፡ ፰፻፲፪ ፡ ፰፻፲፫ ፡ ፰፻፲፭ ፡ ፰፻፲፯ ፡ ፰፻፲፰ ፡ ፰፻፳፱ ፡ .. ብዙ ጊዜ
ኑኖ ደ. ኩንሃ ፡ ፭፻ ፺፰
ኒኮላ ማኪያቬሊ ፡ ፬፻፬
ናስር አድ ዲን ፡ ፯፻፵፭ ፡ ፯፻፵፪ ፡ ፯፻፵፯ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
ናስር (ገራድ) ፡ ፭፻ ፺፭
ናቡከደነፆር ፡ ፭፻፵፰
ናታን ፡ ፲፯
ናዖድ (ዓፄ) ፱ ፡ ፲፫ ፡ ፳፪ ፡ ፴፪ ፡ ፸፬ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ናዖድ ሞገሳ (እቴጌ) ፶ ፡ ፸፯ ፡ ፪፳፯ ፡ ፪፴፭ ፡ ፪፴፰ ፡ ፪፶፭ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ናፖሊዮን ፡ ፭፻፸፯ ፡ ፯፻፭ ፡ ፯፻፱ ፡ ፯፻፶፫ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ንዋየ ማርያም (ዓፄ) ፻
ንዋየ ክርስቶስ (ዓፄ) ፻
ንፍታሌም (አባ ዘደብረ መገራ) ፡ ፭፻፴

...አ...

አሊ (ከሊፋ) ፺፭
አህመድ ቤን ኢብራሂም (ይማም) ፻፲፯ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፸፫ ፡ ፻፸፯ ፡ ፻፸፰ ፡ ፻፹፪ ፡
፫፻፳፪ ፡ ፫፻፳፫ ፡ .... ብዙ ጊዜ

ISIC

አህመድ (ሱልጣን) ፻፺፰
አህመድ (ነጋድ ራእስ) ፵፰
አህመድ ቤን ኢስማኤል ፰፻፹፰
አህመድ ቤን ሶለይማን ኤል ማህሪ .... ፰፻፺፯
አህመድ አሊ ሻሚ ፤ ፻፸፬
አህመድ (ሼክ) ፤ ፻፸፪
አህሙሾ (ገራድ) ፤ ፺፬ ፤ ፬፻፰ ፤ ፬፻፲፭ ፤ ፬፻፺፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አሊ ቤን አቡታሊብ .... ፻፸፪
አልሐጅ .... ፫፻፷፭
አልመቅህ (አልመቅህ) ... ፷
አልማሌክ አልአስራፍ ቃንሺህ አልጋውሪ ፤ ፺፭ ፤ ፺፷ ... ብዙ ጊዜ
አልማሊክ አልአስራፍ (ካይትባያ) ፤ ፺፪ ፤ ፺፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አልቫሬጽ (ፍራንቼስኮ) ፣ ፴፯ ፣ ፴፱ ፣ ፵ ፣ ፵፭ ፣ ፵፪ ፣ ... ብዙ ጊዜ
አልቫሬጽ ካብራል (መርከበኛ) ፣ ... ፶፱
አልቤር ካሜሬር ፤ ፻፵፭ ፤ ፯፻፲፪ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አልታየ (ወይዘሮ) ፤ ፹፷
አልነጋሽ (አህመድ ኤን ነጋሽ) ፬፻፸፪
አል እስራድ ባርስቤይ ፤ ፺፪
አልዛሂር ካንማክ ፤ ... ፺፪ ISIC
አልአዛር ዲ. አንድራዴ ....... ፻፴፯
አልጋውሪ (ሱልጣን) ፤ ፸፭ ፤ ፺፭ ፤ ፺፪ ፤ ፺፷ ፤ ፻፳ ፤ ፻፶፷ ፤ ... ብዙ ጊዜ
አልቡኬርክ (አልፎንስ) ፤ ፶፱ ፤ ፷፯ ፤ ፸ ፤ ... ብዙ ጊዜ
አልፎንሱ ደ. ፓይቫ ....... ፷፪ ፤ ፯፯ ፤ .. ... ብዙ ጊዜ
አልፎንስ ካልዶይራ ..... ፯፻፵፫
አመተ ጊዮርጊስ .... ፹፪
አቡን ቤን አዴከ (ገራድ) ፤ ፻፸፭ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አብዱላሂ (አሚር) ፴፯ ፤ ፷፻፴፯ ፤ ፷፻፴፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አማኑኤል ዶጋማ .... ፰፻፰
አማኑኤል (የፖርቱጋል ንጉሥ ሀብታሙ) ፤ ፲፫ ፤ ፴፯ ፤ ፷፭ ፤ ፷፪ ፤ ፷፫ ፤ ፷፯ ፤ ፷፷ ፤
፸፱ ፤ ፻፯ ፤ ፻፲፭ ፤ ፻፴፭ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አምሐ ጽዮን ..... ፻፷፬
አምሐየስ .... ፯፻፴፷
አሪያስ ዲያዝ .... ፯፻፵፫
አሪስቶት (አሪስቶትል) ፳፯ ፤ ፴፯ ፤ ፺፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
አራድ (የይማም አሽከር) ፤ ፪፻፴፪
አርማሕ (አረመሐ ንጉሥ) .... ፬
አርባ ሺመል .... ፻፺፰ ፤ ፪፻፺፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ

አርማህ (እለ ጸሐም እለ ገበዝ) . . . . ፩፻፸፪
አስታር . . . . ፰
አበበ አረጋይ (ራስ) ፩፻፵፩
አቡሻክር . . . . ፻፷፱
አቡቂር . . . . . ፫፻፲፰
አቡበክር (ሱልጣን) ፻፸፩
አቡበክር ቀጢን ፣ ፺፩ ፣ ፪፻፹፪ ፣ ፫፻፷፩ ፣ . . . ብዙ ጊዜ
አቡበክር (ሸሪፍ) ፻፸፪
አቡበክር (ከሊፋ) ፺፰
አቡበክር ኢብን መሐመድ ሻንባል በአልዊ ፣ . . . . . . . ፵፮
አቡበክር (ኩሽም) ፭፻፰
አቡበክር ኤስባዲቁን . . . . . . . ፻፸፪
አባስ ቤን አቡን (ወዚር) ፩፻፶፰ ፣ ፩፻ ፺ ፣ ፩፻ ፺፯ ፣ ፭፻፩ ፣ ፭፻፶ ፣ . . . ብዙ ጊዜ
አብርሃ ወአጽብሃ ፣ ፭፻፴፱ ፣ ፯፻፴፩ ፣ . . . . . . . ብዙ ጊዜ
አብሰማ ኑር ፣ ፻፷፱ ፣ ፫፻፲፯ ፣ ፩፻፹፱ ፣ ፩፻ ፺፫ ፣ . . . . ብዙ ጊዜ
አብዲናጎ ፣ ፻፷፪ ፣ ፻፶ ፣ ፻፶፪ ፣ ፫፻፶ ፣ . . . . . ብዙ ጊዜ
አብድ ኢን ናስር ፣ ፺፩ ፣ ፩፻፷፯ ፣ ፩፻፴፩ ፣ ፩፻፴፱ ፣ . . . . . . ብዙ ጊዜ
አታቱርክ . . . . ፻፲፩
አትናቴዎስ . . . . ፯፻፷፯


ISIC


አንበሳ ውድም (የድል ነጓድ አባት) ፣ ፲፫
አንቷን ፈርናንዴዝ . . . . . ፭፻፷፫
አንቶኒዎ ዶ. ሲልቬይራ . . . . ፭፻ ፺፰
አንድራዴ . . . . ፺፱
አንጥያኮስ ፬ኛ . . . . ፭፻፴፰
አኖርዮስ (አባ አኖሬዎስ) ፣ ፲፰ ፣ ፹ ፣ . . . . . ብዙ ጊዜ
አኪል ቤን አቡ . . . . ፻፸፰
አከዓብ . . . . ፻፰፪
አውራይ ቃት ዑመር . . . . ፩፻፴፰
አውራይ አህመድ ዲን . . . . ፩፻፹፰
አውሳብዮስ (አባ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ) . . . . ፷፮
አውግስጦስ ቄሣር . . . . ፷፰
አውግስጦስ ዲልማን . . . . ፯፻፲፱
አዩቢት . . . . . ፺፯
አይባክ (የማመሉክ ወገኖች ሱልጣን) . . . . . ፺፯
አይዙር (ንጉሥ) ፷
አደራስ ዲገ . . . . ፻፴፯

አዲ ንእማን (ታሪክ ጸሐፊው) ፺፬
አዳሉ (አዝማች)፤ ፩፻፴፭፤ ፩፻፴፯፤ ፩፻፵፤ .... ብዙ ጊዜ
አዳሙ .... ፺፬
አዶሌ (ወዚር)-አዝማች)፤ ፩፻፲፯፤ ፩፻፲፱፤ ፩፻፲፬፤ ፩፻፲፭፤ ፩፻፲፯፤ ፩፻፲፰፤ ፩፻፲፱፤
፩፻፳፩፤ ፩፻፳፫፤ .... ብዙ ጊዜ
አግብአ ጽዮን (የድል ነዓድ የልጅ ልጅ)፤ ፲፱፤ ፲፫፤ .... ብዙ ጊዜ
አፈወርቅ ፴፯
አፈወ ድንግል (ሊቀ ሠራዊት) ፴፱
ኡመር ዲን (ሱልጣን) ፭፻፸፰
ኡመር (ከሊፋ) ፺፭
ኡመር ቢን አልከታብ .... ፻፸፱
ኡስማን (ከሊፋ) ፺፭
ኡመር ወላስማ .... ፻፤ ፻፳፯፤ .... ብዙ ጊዜ
ኢብራሂም ኤልቃዚ (ገራድ የግራኝ አባት)፤ ፻፸፩፤ ፻፸፯፤ .... ብዙ ጊዜ
ኢብራሂም (መላከተኛ) .... ፳፯
ኢብን ካለኡን ፺
ኢብን አያስ (ግብፃዊ)፤ ፻፺፰
ኢትዮጲስ .... ፩፻፸፫
ኢኛሲዮ ደ. ሎዮላ ........ ፻፶፯
ኢየሱስ ሞዓ (አባ የሐይቅ መምህር)፤ ፻፤ ፯፤ ፱፤ ፲፫፤ .... ብዙ ጊዜ
ኢያሱ (ልጅ) ፩፻፸፫
ኢያሱ (ዓፄ፤ አድያም ሰገድ)፤ ፲፩፤ ፲፱፤ ፹፱፤ ፻፳፱፤ ፻፴፩፤ ፫፻፳፤ ፫፻፵፤ ...
ብዙ ጊዜ
ኢያሱ (ብርሃን ሰገድ ዓፄ) ፩፻፹፱፤ ፭፻፶፩፤ .... ብዙ ጊዜ
ኢያሱ (የእስራኤል መስፍን) .... ፳፩
ኢዮብ .... ፳፩
ኢዮአራም፤ ፯፻፲፩
ኢዮአስ (ዓፄ) ፻፴፩
ኤልማያ .... ፱፻፳፩
ኤልዛቤል ..... ፻፳፱
ኤልያስ (ነቢዩ ይሆን ?)፤ ፻፳፱
ኤዲን አህመድ .... ፵
እለ ዓሚዳ ... ፲፱
እሌኒ ንግሥት (እቴጌ አድማስ ሞገሳ)፤ ፴፱፤ ፳፱፤ ፳፫፤ ፳፬፤ ፳፯፤ ፳፰፤ ፳፱፤ ፸፩፤
፸፯፤ ፻፩፤ ፻፯፤ ፻፲፫፤ ፻፲፭፤ ፻፳፤ ፻፳፯፤ .... ብዙ ጊዜ
እስላም ሰገድ (ራስ) ፱፤ ፸፯፤ ፭፻፭፤ .... ብዙ ጊዜ

እስማኤል (ከዲብ) ፰፻፴፩ ፡ ፰፻፴፯ ፡ ፰፻፴፰
እስክንድር (ታላቁ) ፹፭ ፡ ፹፩ ፡ ፺፰ ፡ .... ብዙ ጊዜ
እስክንድር (ዓፄ) ፴፪ ፡ ፰፪ ፡ ፰፬ ፡ ፻፭ ፡ ፺፬ ፡ ፪፭ ፡ ፪፪ ፡ ፪፯ ፡ ፪፴ ፡ ፪፴፭ ፡ ፪፵፭ ፡
.... ብዙ ጊዜ
እስጢፋኖስ ደጋማ ፡ ፭፻ ፺፫ ፡ ፮፻፫ ፡ ፮፻፭ ፡ ፮፻፰ ፡ ፮፻፱ ፡ ... ብዙ ጊዜ
እስጢፋኖስ ፖልሃርት ፡ ፻፴፮
እንድርያስ አቢዩዶ ፡ ፯፻፴፮ ፡ ፯፻፹፱ ፡ ፯፻፹ ፡ ፯፻፹፪ ፡ ...... ብዙ ጊዜ
እንጦንዮስ (ቅዱስ) ፭፻፯
እድም አሰግድ .... ፲፪
እሪያስ ያዲዝ ...... ፮፻፺፫
ኦትማን (ኡስማን የቶግሩል ልጅ) ፺፮

...ከ...

ኩርድ .... ፺፯
ኩሽም አቡበከር ..... ፪፻፵፩
ኪሎሌ ... ፩፻፹፰
ኪዳነ ወልድ (አለቃ) .... ፭፻፹፭
ካሌብ (ዓፄ) ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ፡ ፵፩ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ካስታንሖዳ .... ፪፬ ፡ ፪፲፰ ፡ ፪፰ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ISIC
ካብራል .... ፺፬
ካግማሀ (ሱልጣን) ፡ ፺
ካራፕስ .... ፩፻፹፬
ክርስቶፎሮስ ደጋማ ፡ ፻፴፪ ፡ ፮፻፯ ፡ ፮፻፲፭ ፡ ፮፻፲፯ ፡ ፮፻፹፪ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ኮንቲ ሮሲኒ (ሙሴ) ፡ ፲፪ ፡ ፫፻፰ ፡ ፫፻፹፬ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ኮጀ መሐመድ .... ፭፻ ፺፬

...ወ...

ወለተ ቅዱሳን .... ፻፪
ወለተ ቀለምሲስ ..... ፪፻፹፭
ወሊንግተን (ጀኔራል) .... ፮፻፭
ወልደ ሃይማኖት (ታሪክ ጸሐፊው) ፡ ፻፩ ፡ ፭፻፺፬
ወልደ ሥላሴ .... (ራስ) ፵፯
ወሰን ሰገድ (ራስ) .... ፲፭ ፡ ፩፻፴፯ ፡ ፩፻፵፪ ፡ .... ብዙ ጊዜ
ወሰንጌ (ተኝ ጌታ) .... ፩፻ ፺፯

ወናግጃራ ....... ፯፻፵፪

ወርቅነህ ወልደማኑኤል ....(ደጃዝማች).... ፪፻፷፩

ወናግ ዣን (ከዳተኛው) ፣ ፬፻፳፯ ፣ ፩፻፵፭ ፣ ፭፻፹፩ ፣ ....... ብዙ ጊዜ

ወዚር ሲና ...... ፺፰

ወዳጆ (ራስ) ፣ ፲

ዊልያም (ራይት) ፪፲፰

ውርጂ አቡን .... ፩፻፶፰

ውድም ረዓድ (ዓፄ) ፣ ፲፯ ፣ ፷፱ ፣ .... ብዙ ጊዜ

...ዐ...

ዑዝ ድሜር (ፓሻ) ፣ ፯፻ ፶፯ ፣ ፯፻ ፶፯ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዒዛና (አብርሃ) ፣ ፯ ፣ ፲፪ ፣ ፩፻፷፪ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዓሊ (ራስ) ፣ ፭፻ ፶፱

ዓሊ (የሰዓድ አድ ዲን ልጅ) ፣ ፻

ዓምደ ሚካኤል (ቢትወደድ) ፣ ፫፻፲፭

ዓምደ ጽዮን (ዓፄ) ፣ ፯ ፣ ፱ ፣ ፲፫ ፣ ፲፯ ፣ ፲፱ ፣ ፵ ፣ ፵፭ ፣ ፵፪ ፣ ፵፰ ፣ ፷፱ ፣ ፺ ፣ ፺፪ ፣

፺፰ ፣ ፻ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዓሥራት (አባ) ፺፰

ዓረብ ፋቂህ ፣ ፵ ፣ ፺፩ ፣ ፷፭ ፣ ፻፩ ፣ ፫፻፲፱ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዓሮን (አዝማች) ፣ ፻፵፯ ፣ ፫፻፲፱ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ዓይበስ ለሐፄ ፣ ፬፻፳፪ ፣ ፩፻፹፫ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዕንባቆም (እጨጌ) ፣ ፲፭ ፣ ፵፭ ፣ ፻፲፯ ፣ ፻፰፱ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዕዝራ (ነቢይ) ..... ፰፩

...ዘ...

ዘሐርቡይ መሐመድ ፣ ፩፻፳፯ ፣ ፩፻፳፰ ፣ ፩፻፳፱ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዘሩባቤል ..... ፰፩

ዘርዓ ያዕቆብ (ዓፄ) ፣ ፱ ፣ ፲፫ ፣ ፳ ፣ ፵ ፣ ፵፪ ፣ ፵፰ ፣ ፵፭ ፣ ፵፯ ፣ ፳፭ ፣ ፳፫ ፣ ፹ ፣

፹፱ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዘርዓ ሠናይ .... ፯፻፲፭

ዘቢድ ፓሻ ፣ ፺፩ ፣ ፹፪ ፣ ፻፰ ፣ ፭፻፹፭ ፣ ፯፻፳፭ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ዘክርስቶስ .... ፫፻፷፭

ዘውዲቱ (ንግሥት) ፣ ፺ ፣ ፺፪ ፣ ፹፯ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ISIC

...ዠ...

ዠሮኔሞ ደሰዛ .... ፻፬
ዠሮም (አባ ቅዱስ)፤ ፹፭፤ ፻፳፭፤ .... ብዙ ጊዜ
ዠአአ ሲልቬይራ ... ፭፻፳፭
ዤሮም ሎቦ ..... ፯፻፹ ፣ ፯፻ ፺፬ ፣ ...... ብዙ ጊዜ
ዣን መንግሣ .... ፸፬
ዣን ቀንጠፋ .... ፹፩
ዣን ቴምፖራል .... ፳፮፤ ፻፴፪፤ ፭፻፲፫፤ ፭፻፲፯፤ .... ብዙ ጊዜ
ዣን አሞራ ... ፹፩፤ ፭፻፸፪፤ .... ብዙ ጊዜ
ዣን ዘላቅ ..... ፻፳፩
ዣን ደካስቴይ (የኤስፓኝ ንግሥት) ........ ፭፻፳
ዣን ጸገና ..... ፭፻፸፪
ዦርዥ ዳብረ (ደ. አብሬው) ፣ ፻፲፭ ፣ ፻፳፩ ፣ ፻፵፭ ፣ ፻፶ ፣ ... ብዙ ጊዜ

...የ...

የማን ክርስቶስ (ራስ)፤ ፲
የሱፍ (ሐጂ)፤ ፻፴፰
ዩልዮስ ቄሣር ፣ ፰
ዩስጥንያኖስ .... ፶፯
ያሬድ (ባለዜማ) ..... ፯፻፳፯
ያኪም .... ፬፻፴፱
ያዕቆብ (የዓፄ ልብነ ድንግል ልጅ)፤ ፹፪፤ ፻፳፫፤ .... ብዙ ጊዜ
ያዕቆብ (ዓፄ) .... ፺
ያዕቆብ (የድል ነአድ ዘር)፤ ፲፪
ያፌት ፯፻፸፭
ይምርሐነ አብ (የንቡረ እድ ይስሐቅ ጓደኛ)፤ ፵፪
ይስሐቅ (ዓፄ) ፲፭፤ ፵፰፤ ፺፤ ፺፰፤ ..... ብዙ ጊዜ
ይስሐቅ (ባሕር ነጋሽ) ፯፻፲፭፤ ፺፻፲፭፤ ፳፻፳፩፤ .... ብዙ ጊዜ
ይስሐቅ (ንቡረ ዕድ)፤ ፵፪፤ ፵፭፤ .... ብዙ ጊዜ
ይኩኖ አምላክ (ተስፋ ኢየሱስ)፣ ፪፣ ፯፣ ፺፣ ፬፣ ፲፩፣ ፵፯፣ ፵፪፣ ፵፭፣ ፵፯፣ ፵፯፣
፻፣ ፻፵፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐኒ (አባ)፤ ፫፻፸፯
ዮሐንስ ሳባ (አረጋዊ መንፈሳዊ)፤ ፳፯፤ ፵፭፤ .... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ (ጃባኒ) ቄስ፤ ፳፰፤ ፸፤ .... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ ኤሽኮላር ... ፻፵፩፤ ፯፻፹፯ .

ISIC

ዮሐንስ መደብር .... ፻፹፱
ዮሐንስ (ዓፄ) ደጃች ካሣ) ፤ ፬፻ ፺፪ ፤ ፭፻፸፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ (ቄስ) ፤ ፳፭ ፤ ፸፬ ፤ ፹፭ ፤ ፻፲ ፤ ፻፴፭ ፤ ፻፵፬ ፤ ፻፳፪ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ ጎሜዝ ..... ፳፫
ዮሐንስ (አዝማች) ፤ ፭፻፴፭ ፤ ፭፻፶ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ (የፖርቱጋል ንጉሥ) ፤ ፩ኛውና ፪ኛው ፤ ፶፮
ዮሐንስ (አባ ፤ ጳጳስ) ፤ ፹፱
ዮሐንስ (ዓፄ ጻድቁ) ፤ ፶፭ ፤ ፭፻፺፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ (ወንጌላዊ) ፤ ፳፭ ፤ ፳፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ፳፯ ፤ ፻፲፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ (ዓፄ ፤ ፬ኛ) ፤ ፹፭
ዮሐንስ (፫ኛ) ፤ ፳፭ ፤ ፸፯ ፤ ፻፵ ፤ ፻፵፭ ፤ ፻፵፪ ፤ ፻፳ ፤ ፻፳፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ ፪ኛ ፻፯ ፤ ፻፵፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሐንስ አባ (የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት) ፤ ፺
ዮሳብ (አባ) ፤ ፯፻፹፭ ፤ ፯፻ ፺፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዮሳፍጥ ..... ፻፲፫
ዮናዳብ (የንጉሥ አዝማች) ፤ ፬፻፹፭ ፤ ፫፻፹፪
ዮና ቦጋለ ፤ ፯፻፯
ዮዲት (የጌዲዎን ልጅ) ፤ ፪ ፤ ፵ ፤ ፫፻፴፯ ፤ ፫፻፸፬ ፤ ፭፻፵ ፤ ፭፻፵፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ ፤
ISIC

...ደ...

ደርደር (ደራደር) የኡመር ወላስማ ልጅ ፤ ....... ፻፸፫
ደርቡሽ .... ፭፻፸፯
ደገልሃን (ደጋልሃን ራስ አዛዥ አዝማች) ፤ ፻፺ ፤ ፻፺፭ ፤ ፻፺፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ደጐል (ጄኔራል ሻርል) ፤ ፪፻፭
ዲልማን (ፕሮፌሰር) ፤ ፲፪
ዲዩጎ ሎፔዝ ፤ ፻፲፭ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፵ ፤ ..... ብዙጊዜ
ዲዮስቆሮስ ፤ ፯፻፳፫ ፤ ፯፻፳፱ ፤ ፯፻፴፭ ፤ ፯፻፴፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዲዮቅልጥያኖስ ..... ፯፻፴፪ ፤ ፯፻፴፫ ፤ ....... ብዙ ጊዜ
ዳዊት (የእስራኤል ንጉሥ) ፤ ፲፪ ፤ ፲፫ ፤ ፲፬ ፤ ፳ ፤ ፳፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዳልሚደዳ ፤ ፭፻፹፭
ዳሚያኑስ ደ. ጎኤዝ (ፖርቱጋላዊ) ፤ ፭፻፯
ደቪንቺ (ሌዎናርዶ) ፤ ፴
ዴካርትስ .... ፳፫
ድልበ ኢየሱስ (ድል በኢየሱስ ?) ፤ ፪፻፳፫ ፤ ፭፻፫ ፤ ፭፻፹፫ ፤ ፭፻፹፱ ፤
፯፻፵ ፤ ፯፻፳፪ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

ድልነዓድ ፤ ፪ ፤ ፯ ፤ ፲፭ ፤ ፲፪ ፤ ፲፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ድል ወንበራ (ባቲ) ፪፻፴፩ ፤ ፬፻፶ ፤ ፬፻፹፭ ፤ ፬፻፺፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ድሮወ ፤ ፲፪
ዶሚኒክ (አባ) ፤ ፻፹፭
ዶም ሉዊዝ ዶ. ሜኔዜስ (ዶመኔዝስ) ፤ ፻፶፩
ዶም ማርቲኖ .... ፭፻፬ ፤ ፭፻፲፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዶም ኤድዋርድ ጋልቫም ..... ፻፯
ዶሪ (ባሕር ነጋሽ) ፤ ፵፰ ፤ ፶ ፤ ፻፲፪ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፹፭ ፤ ፻፹፯ ፤ ፻፶ ፤ .... ብዙ ጊዜ


...ጀ...


ጀምስ ብሩስ ፤ ፯፻፶፯ ፤ ፯፻፳፩ ፤ ፯፻፳፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ጀዎባኒ ፊርናንዴዝ ፤ ..... ፻፯
ጃውሂር (የንጉሥን ባንዲራ ያዥ) ፤ ፬፻፳፰


...ገ...


ገላውዴዎስ (ዓፄ) ፤ ፹፪ ፤ ፹፯ ፤ ፴፩ ፤ ፴፪ ፤ ፴፭ ፤ ፴፰ ፤ ፴፱ ፤ ፵፯ ፤ ፶፩ ፤ ፶፭ ፤ ፷፭ ፤
፷፱ ፤ ፺፪ ፤ ፺፬ ፤ ፻፲፰ ፤ ፻፴፪ ፤ ፻፳፫ ፤ ፻፷ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ገላውዴዎስ (ሰማዕት) ፤ ፴፪

ISIC

ገማልዲን መሐመድ .... ፪፻፵፱
ገሪማ (አባ) ፤ ፭፻
ገብረ መስቀል (ዓፄ) ፤ ፺፯ ፤ ፫፻፷፯ ፤ ፯፻፹፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ገብረ ማርያም (እንጥረኛው) ፤ ፻፴፯ ፤ ፻፴፯ ፤
ገብረ ሥላሴ ፤ ፭፻፺ ፤ ፭፻፺፬ ፤
ገብረ እንድርያስ (አባ) ፤ ፻፪ ፤ ፻፬ ፤ ፻፭ ፤ ፫፻፹፱ ፤ ፭፻፺፩ ፤ ፭፻፵፩ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ገብረ ሥላሴ (ጸሐፌ ትእዛዝ) ፤ ፴፭ ፤ ፴፯ ፤ ፻፳፩ ፤
ጉይዲ (ኢኛሲዮ) ፤ ፬፻ ፶፯
ጊዮርጊስ (አባ) ፤ ፻፴፯
ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ፤ ፻፳፱ ፤ ፬፻ ፶፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጋሌሎዎ (ጋሊ ሌይ) ፤ ፹፰
ጋልቫም (አለቃ) ፤ ፻፯
ጋማል አድ ዲን (ገመልዲን) ..... ፻
ጋስፓር ሱሬያኖ ፤ ፭፻፹፫
ጌታሁን ማሜ ፤ ፶፩
ጌዴዎን (የፈላሾች መሪ) ፤ ፪ ፤ ፭፻፵ ፤ ፭፻፵፬ ፤ ፭፻፳፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ግርማ በሻህ (አቶ) ፤ ፻፵፪

ጎርጎርዮስ (ቅዱስ) ፤ ፴፯
ጎይታ አላህ መጀን .... ፱፻፹፱
ጎይታ ኑር ..... ፫፻፶፱
ጎይታ ኡስማን ..... ፱፻፰
ጉሹ (ራስ) ፤ ፲
ጉሹ (ጀሹ ገራድ) ፤ ፩፻፶፰ ፤ ፩፻፶፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ

...ጠ...

ጠሊላ .... ፮፻፹፯ ፤ ፮፻፹፱ ፤ ፮፻ ፺፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጢጦስ (ቂሣር) ፤ ፳፰
ጣይቱ (እቴጌ) ፤ ፹፰ ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፴፬ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

...ጨ...

ጫላ (አዛዥ) ፤ ፱

...ጰ...

ጲላጦስ .... ፳፰ ፤ ፰፻፴፯ ፤ .. ብዙ ጊዜ
ISIC
ጳውሎስ (ሐዋርያ ቅዱስ) ፤ ፳፰ ፤ ፳፰ ፤ ፴፯ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፵፫ ፤ ፰፻፲፫ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ጴጥሮስ (ሐዋርያ ቅዱስ) ፤ ፳፰ ፤ ፰፻፲፫ ፤ ፰፻፲፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጴጥሮስ (ሊቀ ጳጳስ ፤ የእስክንድርያው) ፤ ፻፳፱
ጴጥሮስ (እጨጌ) ፤ ፻፲፯

...ጸ...

ጸጋ ዘአብ (አባ) ፤ ፻፴፮ ፤ ፻፶፬ ፤ ፻፶፱ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ጽንፈ አርዕድ .... ፲፫
ጽዮን ሞገሳ (እቴጌ) ፤ ፻፴

...ፈ...

ፈርዖን ... ፴፯
ፈርናኦ ካርዶዞ ..... ፮፻፹፩
ፈቅጦር (ቅዱስ) ፤ ፸፰ ፤ ፫፻፲፬ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ፈልክስዩስ .... ፳፯
ፊልጶስ (እጨጌ) ፤ ፲፯ ፤ ፹
ፊልጶስ (ዳግማዊ) ፤ ፻፴፱

ፊቅጦር (አቤቶ)፤ ፹፪፤ ፪፻፳፫፤ ፭፻፳፪፤ ፭፻፹፬፤ ፭፻፸፱፤.... ብዙ ጊዜ
ፊንሐስ ... ፲፭
ፋራቃሃም ሳቁ ፡ ፪፭፱
ፋራቃሃም ዲን ፤ ፬፻፭፯
ፋሪቃሃም ዓሊ ፤ ፫፻፭ ፤ ፫፻፹፭ ፤ ፬፻ ፺፱ ፤.... ብዙ ጊዜ
ፋሲል (ዓፄ)፤ ፹፭፤ ፫፻፶፯፤.... ብዙ ጊዜ
ፋሲለደስ (አቤቶሁን)፤ ፴፩
ፋኑኤል (የደዋሮ ገዥ)፤ ፪፻፳፫ ፤ ፪፻፸፩ ፤ ፪፻፸፱ ፤.... ብዙ ጊዜ
ፈርዳውሳ (የግራኝ እህት)፤ ፪፻፸፭
ፍላቭያኖስ (ቂሣር)፤ ፪፻፭፭
ፍራንሷ (፩ኛ) የፈረንሳይ ንጉሥ ፡ ፭፻፵፫
ፍሬ ማርያም (እቴጌ)፤ ፪፴
ፍቅረ ኢየሱስ ዋሹ (ጕሹ)፤ ፪፻፲፯

...ፐ...

ፒዬር ደ. ሌዎን .... ፯፻፫
ፒዬር ቴሎዝ ..... ፵፩
ፒየትሮ አልፎንሶ ሜንዲዝ .... ፪፯

ISIC

ፔሪክል ..... ፶፯
ፓቼሩ .... ፭፻ ፺፭
ፔሬዝ ..... ፶፱
ፔሬይራ ....... ፬፻፳፪
ፔድሮ ደ. ኮቪልሐእ ፡ ፴፯ ፡ ፵፪ ፡ ፳፫ ፡ ፪፻፵፰ ፡ ፪፻፵፱ ፡ ፭፻፲፯ ፡...... ብዙ ጊዜ
ፐላቶን .... ፳፯ ፤ ፶፯ .... ብዙ ጊዜ

# ያገርና የቦታ ዝርዝር

## ...ሀ...


ሂሚያሪት ፤ ፮ ፤ ፬፻፸፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሃሌሎ ..... ፭፻፳፯ ፤ ፭፻፳፱ ፤ ፭፻፴ ፤ ፭፻፴፩ ፤
ሃድያ .... ፬፻፳፭ ፤ ፬፻፴ ፤ ፬፻፴፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሂጃዝ (ሂጋዝ) ፤ ፻፹፰
ሂጃ .... ፷፰
ሆርሙዝ ..... ፺፱ ፤ ፻፺፫ ፤ ፻፺፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሆባት (ሐባት ዘበርታ) ፤ ፻፷፩ ፤ ፻፸፱ ፤ ፻፸፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ


## ...ለ...


ለጋሶ .... ፭፻፳፯ ፤ ፭፻፴ .....
ሊስቦን ...... ፴፱ ፤ ፷፯ ፤ ፻፲፫ ፤ ፻፲፭ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፴፯ ፤ ፻፺፱ ፤ ....... ብዙ ጊዜ
ሊዚታንያ (ሉዚታንያ) ፤ ፺፯
ላሊበላ ፤ ፴፱ ፤ ፻፸፫ ፤ ፫፻፹፬ ፤ ፬፻፷ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ላስታ ፤ ፱ ፤ ፮ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ሎንዶን ፤ ፻፳፬ ፤ ፻፹፯ ፤ ፫፻፸፫ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ISIC

## ...ሐ...


ሐማሴን ..... ፰
ሐመጃ (ሐሙጅ) ፤ ፭፻፴፱
ሐረርጌ (ሐረር) ፤ ፵፯ ፤ ፸፭ ፤ ፻ ፤ ፻፩ ፤ ፻፸፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሐንጋሪ .... ፺፯ ፤ ፻፲፱ ፤
ሐዊያ (ሱማሌ) ፤ ፻፸፬
ሐውዜን .... ፰
ሐይቅ እስጢፋኖስ ..... ፫፻ ፺ ፤ ፬፻፷፬ ፤ ፬፻፷፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሐድራሞት ፤ ፭፻፹፭ ፤ ፭፻ ፺፭ ፤ ፭፻ ፺፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ሐድያ (ባደጎ) ፤ ፹ ፤ ፹፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሐድያ (ከምባታ) ፤ ፹፩ ፤ ፻፴ ፤ ፬፻፴ ፤ ፬፻፴፩ ፤ ፬፻፵፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ሐን (ሁጉዋ) ፤ ፫፻፷፯ ፤ ፫፻፷፰ ፤ ፫፻፹፰ ፤ ....... ብዙ ጊዜ
ሕንድ ውቅያኖስ .... ፻፷፭
ሕንድ ፤ ፺፩ ፤ ፺፱ ፤ ፷፩ ፤ ፷፱ ፤ ፷፬ ፤ ፸፯ ፤ ፻፲፩ ፤ ፻፴፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

...መ...

መለሳይ (የነገድ ስም) ....... ፪፻፳ ......... ብዙ ጊዜ
መርጡለ ማርያም ፤ ፪፻፷፯ ፤ ፪፻፴ ፤ ፪፻፴፮ ፤ ፫፻፹፩ ፤ .... ብዙ ጊዜ
መራቤቴ ... ፹፩
መስኮብ ..... ፺፱
መቁት (ደጋ መቂት) ፤ ፭፻፭
መቅደላ ..... ፬፻፩
መንዝ ፤ ፱ ፤ ፹፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
መካ (ሜካ ፤ መካ መዲና) ፤ ፪፻፷፬ ፤ ፪፻፴፱ ፤ ፯፻፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
መካነ ማርያም ..... ፱
መካነ ሥላሴ ....... ፱ ፤ ፫፻፸፫ ፤ ፫፻፹፱ ፤ ....... ብዙ ጊዜ
መካከለኛው ምሥራቅ ፤ ፲፯ ፤ ፵፭ ፤ ፺፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
መዲና ..... ፭፻፲፭
መዘጋ ..... ፬፻፹፪
ማሌዚያ ..... ፺፱
ማሮክ ..... ፷፩
ማደጋስካር ...... ፪፻፵፫
ማይጨው ፤ ፫፻፴፱ ፤ ፫፻ ፺፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ISIC
ማካዎ ........ ፺፱
ማውሪታንያ ፤ ፪፻፺፯
ሜሶፖታሚያ ...... ፪፻፴፩
ምሥራቅ ..... ፲፯
ምንጃር ..... ፪ ፺፯
ምችግ .... ፫፻፺፩
ምጥዋ (ምጽዋ) ፤ ፷፪ ፤ ፸፩ ፤ ፸፪ ፤ ፪፻፲፫ ፤ ፪፻፲፭ ፤ ፪፻፲፯ ፤ ፪፻፴፪ ፤ ፪፻፵ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ሞቃዲሾ .... ፪፻፺፱
ሞካ ..... ፭፻ ፺፭
ሞዛምቢክ ..... ፯፻፲፪ ፤ ፯፻፲፩ ፤ ፯፻፸፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

...ሠ...

ሠራዬ ..... ፬፻፷፭ ፤ ፭፻፷፯ ፤ ፯፻፴፫ ፤ ፯፻፴፱ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

...ረ...

ሩማንያ ... ፪፻፷፭
ራያ .... ፹፩

ሮም ... ፶፯ ፡ ፶፯ ፡ ፹፬ ፡ ፶፯ ፡ ፻፳ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፵ ፡ .... ብዙ ጊዜ

ሮዝሬይ .... ፰፻፴፫


...ሰ...


ሰሐጢ .... ፯፻፲፰

ሰመርማ .... ፱፻፲፯ ፡ ፱፻፴ ፡

ሰሜን አፍሪካ ..... ፱

ሰሀርት .... ፯፻፶፯

ሰቆጣ ፡ ፬፻፹፰ ፡ ፰፻፺፬ .... ብዙ ጊዜ

ሰነዓ ....... ፯፻

ሰንዓፌ ..... ፯፻፲፰

ሰዓዲን ፡ ፯፻፴፯ ፡ ፯፻፴፰ ፡ ...... ብዙ ጊዜ

ሱማሌ ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፰ ፡ ፫፻፹ ፡ ...... ብዙ ጊዜ

ሱዋኪን (ሱአኪም) ፡ ፳፻ ፡ ፻፲ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፳፯ ፡ ...... ብዙ ጊዜ

ሱዌዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፰፻ ፶፫ ፡ ፰፻ ፶፯ ፡ ፯፻፱ ፡ ..... ብዙ ጊዜ

ሱዳን .... ፰ ፡ ፰፻፵፰ ፡ ፳፻፰ ፡ .... ብዙ ጊዜ

ሲኖዶስ ..... ፹፬

ሳባ ፡ ..... ፯፻፷፬

ሴርቦ ክሮአት .... ፫፻ ፶፯


ISIC


ስጣንቡል ..... ፯፻፩

ሶቆጥራ .... ፯፻፫

ሶርያ ፡ ፻፩ ፡ ፻፴፬ ፡ ...... ብዙ ጊዜ


...ሸ...


ሸዋ ፡ ፯ ፡ ፻፯ ፡ ፻፴ ፡ .... ብዙ ጊዜ

ሸዋዳ ፡ ፯፻፹፰ ፡ ፯፻፹፬ ፡ ፯፻ ፶፬ ፡ ፯፻፵፬ ፡ ..... ብዙ ጊዜ

ሻምንዝድ ..... ፻፷፱

ሻርካህ ......... ፱፻፹፬

ሽምብራ ኩሬ (ቢሸፍቱ አጠገብ) ፻፷፯ ፡ ፻፹፬ ፡ ፱፻፬ ፡ ..... ብዙ ጊዜ

ሺሬ ፰፻፴፫ ፡ ፰፻፳፳ ፡ ፰፻፳፬ ፡ ፰፻፷ ፡ ...... ብዙ ጊዜ

ሾጃራህ (ሾገራህ) ፡ .... ፫፻፳

## ...ቀ...


ቀይ ባሕር ፣ ፶፮ ፣ ፷፪ ፣ ፸፪ ፣ ፻፰ ፣ ፻፲፪ ፣ ፻፵፫ ፣ ፫፻፹፮ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ቀወት ..... ፫፻፷፬

ቁስጥንጥንያ ፣ ፻፹፬ ፣ ፻፴፩ ፣ ፫፻፲፪ ፣ ፮፻፹፯ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ቂሳሪያ ..... ፫፻፶፱

ቃርቃራህ ፣ (ቀርቀራ) ፣ ፫፻፹፬ .... ፫፻፹፩ ፣ ፫፻፹፬ ፣ ፯፻፹ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ቋራ ..... ፰፻፵

ቆራሮው .... ፬፻፹


## ...በ...


በንኩል ፣ ፰፻፹፯ ፣ ፰፻፹፱ ፣ ....... ብዙ ጊዜ

በጌምድር ፣ ፷ ፣ ፲ ፣ ፻፵፫ ፣ ...... ብዙ ጊዜ

ቡግና ፣ ፻፵፫

ቡርክሎሜዳ ፣ ፰፻፹፰ ፣ ፰፻፹፱ ፣ ፰፻፺ ፣ ፰፻፺፩ ፣ ....... ብዙ ጊዜ

ቡልጋሪያ ....... ፻፷፰

ቡታጅራ ..... ፫፻፲፯

ቢየና .... ፫፻፸፫ ፣ ፷፻፪

ባቢሎን .፣... ፰፻፴፩ ፣ ፰፻፴፷ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ባሊ (ባሌ) ፣ ፷ ፣ ፲ ፣ ፫፻፶፰ ፣ ፫፻፴፷ ፣ ፬፻፵፩ ፣ ፬፻፵፷ ፣.... ብዙ ጊዜ

ባልካን ፣ ፻፷፰

ቫቲካን ፣ ፯፷ ፣ ፯፻፹፪ ፣ ፯፻፵፷ ፣ ፯፻፶፬ ፣ ...... ብዙ ጊዜ

ባብ ኤል መንደብ ..... ፻፴፷ ፣ ፰፻፺፬ ፣ ፺፻ ፣ ፺፻፫ ፣ ...... ብዙ ጊዜ

ባሕር ዳር ..... ፰፻፹፬

ባሕር አምባ ..... ፰፻፵፯

ባሕረ ኤርትራ ..... ፰፻፺

ባደቁ (ከተማ) ፪፻፲ ፣ ፪፻፲፭ ፣ ፬፻፸፭ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ቤተ ማርያም ...... ፬፻፷፬

ቤተ አምሐራ (ሳይንት) ፣ ፻፴፷ ፣ ፻፴፱ ፣ ፻፵ ፣ ፻፶ ፣ ፪፻፲፪ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

ቬኔዚያ ....... ፻፴፯ ፣ ፰፻፺፬ ....... ብዙ ጊዜ

ብራዚል .... ፻፴፷ ፣ ፻፵፱ ፣ ...... ብዙ ጊዜ

ቦራ ..... ፻፵፫

ቦሰት .... ፫፻፴፭ ፣ ፫፻፸፭ ፣ .... ብዙ ጊዜ

ቦካን ..... ፻፷፭ ፣ ፻፷፫ ፣ ..... ብዙ ጊዜ

## ...ተ...

ተሰሎንቄ ..... ፳፮
ተምቤን (ተንቤን) ፤ ፬፻፸፯ ፤ ፬፻፸፱ ፤ ፰፻፳፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ተድባበ ማርያም ፤ ፲
ቱሉ ዲምቱ ....... ፪፻፯
ቱኒዝ ..... ፺፰
ታንጌር ..... ፳፭
ቱርክ ..... ፻፲፭ ፤ ፻፲፮ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፳፮ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፵ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ትግሬ ...... ፳
ትሪፖሊ ..... ፺፰ ፤ (ወደብ)

## ...ቻ...

ቻይና ..... ፺፱

## ...ነ...

ነምሳ ፤ ፵፯ ፤ ፻፴፬ ፤ ፻፳፭ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ነገደ ካም .... ፯
ነገደ እግአዝያን ፤ ፭ ፤ ፯ ..... ብዙ 1316
ነገደ ዮቅጣን (ሴማውያን) .... ፯
ኑብያ ፤ ፺፯ ፤ ፳፪ ፤ ፪ ፤ ፪፲፯ ፤ ፫፻፴፪ ፤ ፫፻፴፬ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ኒቅያ ፤ ፫፻፴፯ ፤ ፯፻፴፭ ፤ ፯፻፴፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ኒው ጊኒ ........ ፺፱
ናቢላ ..... ፬፻ ፯
ናዝሬት ...... ፻ ፺፫

## ...አ...

እምባ ዶርሖ ..... ፺፬
እምባ ግሼን ..... ፲፬ ፤ ፺፬ ፤ ፫፻፵፫ ፤ ፬፻፳ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
እምባ አላጌ ..... ፻፲፯ ፤ ፻፴፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
እምባ ነገሥት ..... ፲፬ ፤ ፪፻፴፯ ፤ ፳፻ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
እምባ ሠነይት (ሰነይት) ፬፻፸፪ ፤ ፬፻፸፯ ፤ ፬፻ ፺፯ ፤ ፯፻፴፭ ፤ ፯፻፵፫ ፤ ... ብዙ ጊዜ
አሜሪካ ..... ፻፴፰
አማራ ሳይንት ፤ ፳ ፤ ፫፻፸፭
አማራ (የአማራ አገር አማርኛ) ፤ ፳ ፤ ፲ ፤ ፲፭ ፤ ፲፬ ፤ ፻፵፫ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

አልጋርቭ .... ፻፹፫ ፡ ፻፺፮ ፡
አድጉብሶ .... ፺፩
አጋሜ ... ፰ ፡ ፻፳፱ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አፍሪካ ፡ ፶፮ ፡ ፶፱ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ፡ ፺፮ ፡ ፻፴፭ ፡ .... ብዙ ጊዜ
አድዋ .... ፴፮
አፋር .... ፬፻፳፯
አዳል ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፰ ፡ .... ብዙ ጊዜ
አዲስ አበባ .... ፻፳፪
አደን .... ፭፻ ፺፭
አጋሜ ... ፬፻፸፭ ፡ ፬፻፸፯ ፡ ፯፻፴፫ ፡ ፯፻፴፭ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አልዠሪ (አልጀሪ) ፡ ፺፰
አሌፕ (ሶርያ) ፡ ፻፭
አሀያ ሬጅ.... ፫፻፺፭ ፡ ፫፻፹፬ ..... ብዙ ጊዜ
አይፈርስ (ዐይፈርስ) ፡ ፱፻፲፭ ፡ ፱፻፸፮ ፡ ፱፻፸፯ ፡ ፱፻፹፭ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አደን (የባሕር ወደብ) ፡ ፻፳፬ ፡ ፭፻፹፯ ፡
አዛኤል .... ፬
አዋሽ (ወንዝ) ፡ ፱ ፡ ፱፻ ፺፮ ፡ ፫፻፳፫ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አውሮፓ .... ፳፱ ፡ ፺ ፡ ፺፮ ፡ ፻፭ ፡ ፻፴፰ ፡ ፻፴፱ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አክሱም ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፳ ፡ ፶፮ ፡ ፶፰ ፡ ፸፩ ፡ ፻S፹፮ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፳፱ ፡ ፻፴፰ ፡ .
ብዙ ጊዜ
አካም ፡ ፻፸፩ ፡ ፱፻፹፯ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አከለ ጉዛይ ..... ፰
አንጾኪያ (የኢትዮጵያ) ፻፲፫ ፡ ፻፲፰ ፡ ፱፻፹፭ ፡ ....... ብዙ ጊዜ
አንጾኪያ (መካከለኛው ምሥራቅ) ፡ ፳፯ ፡ ፴፯ ፡ ፴፫ ፡ ...... ብዙ ጊዜ
አንጎት (አንጐት) ፡ ፻፹፫ ፡ ፻፶ ፡ ፱፻ ፺፩ ፡ ፫፻ ፺፩ ፡ ፬፻፳፯ ፡
አቾፈር .... ፭፻፹፩ ፡ ፭፻፺፩ ፡
አንድሪኖፕል .... ፺፯
አንኮበር .... ፬፻፳፩
አትሮንስ ማርያም .... ፱ ፡ ፻፴፮ ፡ ፫፻፹፯ ፡ ፫፻፹፭ ፡ ፫፻፹፰ ፡ .... ብዙ ጊዜ
አትሪሽ ፡ ፭፻፰
አበርጋሌ .... ፬፻፸
አቅራ ... ፱፻፺፰
አሸንጌ .... ፻፲፯ ፡ ፻፴፭ ፡ ፯፻፹፫ ፡ ..... ብዙ ጊዜ
አሳሆርታ ..... ፰
አርጎባ ..... ፱፻፸፬
አርኪቆ (ሐርኪቆ) ፡ ፻፲ ፡ ፲፩ ፡ ፻፲፭ ፡ ፯፻፱ ፡ ...... ብዙ ጊዜ

አርማጭሆ ..... ፰፻፵

አሩሲ .... ፳ ፤ ፲ ፤ .... ብዙ ጊዜ

አርመን ፤ ፻፲፫ ፤ ፻፳፩ ፤ ፰፻፳፫ ፤

ኡጋንዳ .... ፰፻፵፭

ኡይዝ ..... ፫፻፲

ኢትዮጵያ ፤ ፩ ፤ ፪ ፤ ፯ ፤ ፵፬ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ኢየሩሳሌም ፤ ፴፪ ፤ ፴፫ ፤ ፴፭ ፤ ፳፩ ፤ ፳፬ ፤ ፳፭ ፤ ፳፱ ፤ ፷ ፤ ፻፴፫ ፤ ፻፴፱ ፤ ... ብዙ ጊዜ

ኢጣሊያ ፤ ፶ ፤ ፶፫ ፤ ፶፩ ፤ ፻፴፯ ፤ ፫፻፴፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ኤልማያ (ቀበተኛ ጐሣ) ፤ ፫፻፩

ኤል ካንካ ... ፶፭

ኤርትራ (ባሕረ) ፤ ፯ ፤ ፳ ፤ ፻፴፱ ፤ ፻፶፪ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ኤስፓኝ ፤ ፶፱ ፤ ፶፪ ፤ ፻፴፭ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ኤግባ ሚካኤል ኤግባ ሚካኤል ........ (ዕቁበ ሚካኤል) ..... ፬፻፴፯

ኤዲር (ይፋት) ፤ ፪፻፰

እሥራኤል ..... ፯ ፤ ፲፩ ፤ ፲፪ ፤ ፲፬ ፤ ፳፬ ፤ ፳፭ ፤ ፵፰ ፤ ፵፯ ፤ ፹፰ ፤ ፰፻፹፬ ፤ .. ብዙ ጊዜ

ኤፍራጥስ (ወንዝ) ፤ ፶፭ ፤ ....... ብዙ ጊዜ

እስክንድርያ ፤ ፯ ፤ ፶ ፤ ፻፯ ፤ ፻፳፱ ፤ ፰፻፲፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

እስያ .... ፻፹፪

እስጣምቡል ..... ፶፯ ፤ ፳፻፴፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

እነሴ .... ፻፴፪

እንደርታ .... ፬፻፹፯ ፤ ፰፻፳፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

እናርያ (እናሪያ) ፤ ፰፻፴፩ ፤ ፳፻፴፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

እንደገብጣን ... ፫፻፲፰ ፤ ፰፻፳፬ ፤ .... ብዙ ጊዜ

እንዶኔዚያ ..... ፰፻፪

እንዶጥናሀ (እንጦጦ) ፤ ፫፻፪ ፤ ፫፻፫ ፤ ፫፻፬ ፤ .... ብዙ ጊዜ

እንግሊዝ ..... ፶፱

እንጦጦ ማርያም .... ፻፴፪ ፤ ፯፻፶፱ ፤ .... ብዙ ጊዜ

እንፍራጽ (እንፍራዝ) ፤ ፬፻፶ ፤ ፰፻፰ ፤ .... ብዙ ጊዜ

ኦፌር (ኦርሞ) .... ፯

ኦሞ (ወንዝ) ፤ ፬፻፳፱


...ወ...


ወፍላ .... ፰፻፶ ፤ ፯፻፳፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

ወህኒ አምባ .... ፬፻፬

ወላስማ ፤ ፲፩ ፤ ፻ ፤ ፪፻፴፱ ፤ .... ብዙ ጊዜ

ወልቃኢት ፤ ፩፻፹፭ ፤ ፭፻፵ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ወሎ ፤ ፳ ፤ ፲ .... ብዙ ጊዜ
ወረይሉ (ወረኢሉ) ፤ ፳ ፤ ፫፻፶፫ ፤ ፫፻፹፱ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ወረ ጉራእ .... ፲
ወረ ኖሌ ኢሉ ...... ፲
ወናግ አምባ .... ፪፻ ፺፩
ወረ ከረዩ .... ፲
ወምበረያ (ወምበራ ፣ ወንበራ) ፣ .... ፻ ፺፫
ወጅ (ወንጂ) ፤ ፱ ፤ ፫፻፴፭ ፤ ፬፻፶ ፤ ፬፻፶፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ውጋዴን (ውጋዴን) ፤ ፯ ፤ ፻፸፩ ፤ ፻፸፭ ፤ ፻፸፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዋልድባ ..... ፩፻፹፭
ዋላቅ (ወለቃ) ፤ ፫፻፹፯
ዋስል .... ፫፻፵፯ ፤ ፬፻፶፫ ፤ ፬፻፶፩ ፤ ፬፻፶፭ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ዋጅራት .... ፹፩
ዋግ .... ፻፵፫ ፤ ፭፻፳፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ

...ከ...

ከነዓን (ፓለስቲን) ፤ ፳፩ ፤ ፭፻፴፭ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ISIC
ከፋ .... ፲
ካመራን (ደሴቶች ካምራን) ፤ ..... ፻፳ ፤ ፻፶፪ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ካምቦዲያ .... ፫፻፸፩
ካምብራይ ..... ፳፭ ፤ ፫፻፴፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ካርታኸ ..... (ቱኒስ) ፤ ፪፻፹፫
ካስቲይና .... ፶፯
ካይሮ ፤ ፳፰ ፤ ፻፳፩ ፤ ፻፶፰ ፤ ፯፻፪ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ኬልቄዶን ፤ (ጉባኤ) ፤ ፯፻፴ ፤ ፯፻፴፭ ፤ ፯፻፴፪ ፤ ፯፻፴፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ኬንያ ፤ ፭፻፵፰ ፤ ፭፻፸፫ ፤ ፮፻፳፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ኮምብራ ..... ፳፭
ኮንጎ ..... (ኮንጎ ማኒ) ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፵፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ኮረም .... ፩፻፹፭

...ዐ...

ዓረብ ፤ ፲፪ ፤ ፴፫ ፤ ፴፯ ፤ ፴፰ ፤ ፵ ፤ ፵፭ ፤ ፳፫ ፤ ፳፩ ፤ ፸፯ ፤ ፻ ፤ ፻፭ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ዓስባ .... ፩፻፸፩
ዓባይ (ዓባይ ወንዝ) ፤ ፯ ፤ ፩፻፵፱ ፤ ፩፻፹፭ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዓድዋ .... ፭፻፸፯

...ዘ...


ዘቢድ .... ፻፭ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፳፭ ፤ ፻፺፩ ፤ ፪፻፺፪ ፤ ፯፻፺፯ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዘይላ ፤ ፻፩ ፤ ፻፳፬ ፤ ፻፴፫ ፤ ፻፵ ፤ ፻፵፯ ፤ ፻፵፰ ፤ ፻፶፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዚፋሀ (ከተማ) ፤ ፪፻፬ ፤ ፪፻፭ ፤ ፪፻፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ዛላ አንበሳ ..... ፭፻፺
ዛጉዬ ፤ ፪ ፤ ፷፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዛካ ሲም ..... ፻፷፭
ዛንዚባር ..... ፻፺፱
ዛኪ .... ፻፷፭
ዜዳም (ጀዳ ?) ፤ ፳፰ ፤ ፻፳፬ ፤ ፪፻፷፩ ፤ ........ ብዙ ጊዜ
ዝቋላ .... ፪፻፳፬ ፤ ፪፻፷፱ ፤ ፫፻፳፯ ፤ ፬፻፳፫ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ዝሞን ዱር ፤ ፪፻፵፯ ፤ ፪፻፷፱ ፤ ፫፻፲ ፤ ፭፻፳፬ ፤ ፭፻፳፯ ፤ ፭፻፳፰ ፤ ...
. . ብዙ ጊዜ
ዞብል (ቅዳ አገር) ...... ፮፻፺፮ ፤ ፮፻፹፪ ፤ ፮፻፹፫ ፤ ....... ብዙ ጊዜ
ዞፋሀ ..... ፻፷፪


...ዡ...


ዡንዘላቅ ....... ፪፻፲፭


...የ...


የሐ. ፤ ፪


ISIC


የመን ፤ ፻፳፭ ፤ ፻፷ ፤ ፭፻፺፭ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
የረር ፤ ፫፻፪ ፤ ፬፻፲፫ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
የረርና ከረዩ አውራጃ ..... ፱ ፤ ፫፻፪ ፤ ፫፻፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዩጎስላቪያ ..... ፻፳፭
ያርቲ ሜዳ .... ፮፻፵፬
ይፋት .... ፲፩ ፤ ፳፫ ፤ ፷፭ ፤ ፻፵፪ ፤ ፻፵፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ


...ደ...


ደሆሀር .... ፪፻፳፮
ደሆና .... ፪፻፵፯
ደላንታ .... ፫፻፺፰
ደረስጌ ...... ፮፻፵፯
ደቅ እስጢፋኖስ ....... ፭፻፷፬
ደቡል .... ፻፵፬
ደጀን ..... ፫፻፵፭

ደንቢያ ፤ ፭፻፵ ፤ ፻፵፫ ፤ ፬፻፹፭ ፤ ፭፻፵ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ደዋሮ .... ፻፴ ፤ ፻፴፫ ፤ ፻፶ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ደንቀዝ ፤ ፯፻ ፺፬ ፤ ፯፻፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ደብረ ዳሞ ፤ ፲፫ ፤ ፳፪ ፤ ፳፫ ፤ ፭፻፹፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ደብረ ወርቅ ..... ፹፪
ደባርዋ (ደባሩዋ) ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፳፭ ፤ ፻፶ ፤ ፻፶፩ ፤ ፻፶፪ ፤ ፪፻፴፬ ፤.. ብዙ ጊዜ
ደብረ ከርቤ ፤ ፭፻፳፯ ፤ ፭፻፳፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ደብረ እስጢፋኖስ (ሐይቅ) ፤ ፳ ፤ ፱ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ደብረ ብርሃን ፤ ፳፩ ፤ ፻፲፫ ፤ ፫፻፴፫ ፤ ፫፻፵፪ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ደብረ በንኮል ..... ፭፻፴
ደብረ ቢዘን ፤ ፳፪ ፤ ፻፲ ፤ ፻፲፫ ፤ ፻፲፭ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፵፬ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ደብረ ሊባኖስ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፲፰ ፤ ፻፳፱ ፤ ፻፴፭ ፤ ፻፷፫ ፤ ፻፷፯ ፤ ፻፷፰ ፤ ፫፻፲፱ ፤ ፬፻ ፺፬ ፤
፬፻ ፺፭ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ደብረ ሐይቅ .... ፳፫
ዱከም ወንዝ ፤ ፫፻፩ ፤ ፫፻፪ ፤ ፫፻፬ ፤ ፫፻፯ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ዲው ፤ ፭፻ ፺፬ ፤ ፭፻ ፺፯ ፤ ፭፻ ፺፰ ፤ ፭፻ ፺፱ ፤
ዳህላቅ (ደሴት) ፤ ፻፱ ፤ ፻፲ ፤ ፻፲፩ ፤ ፻፲፭ ፤
ዳሞት .... ፺፩ ፤ ፫፻፱ ፤ ፫፻፲ ፤ ፫፻፲፩ ፤ ፫፻፲፪ ፤ ፫፻፲፫ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ዳካር ..... ፻፹፩ ፤ ፪፻፵፱ ፤ ...... ብዙ ጊዜ ISIC
ዶባ ..... ፹ ፤ ፹፩ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

...ጀ...

ጀጀራህ ..... ፪፻፴፯
ጀኖቫ (ኢጣልያ) ፤ ፭፻፳
ጀርመን ፤ ፺፱ ፤ ፺፩ ፤ ፺፯ ፤ ፻፲፪ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ጂራውራሪ ..... ፬፻፴፯
ጂዛን ...... ፻፸
ጃጋን ...... ፺፪
ጃንጀሮ ..... ፹፩
ጆማ ፤ ፲ ፤ ፯፻፷፭ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

...ገ...

ገሊላ ገዳም ..... ፯፻፴፱
ጉርሱም ..... ፬
ገበርጌ ...... ፫፻፲፪
ጎንተ ጊዮርጊስ ፤ ፫፻፹፯ ፤ ፫፻፹፰ ፤ ፭፻፳፬ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ጎንዝ .... ፻፵፫

ገድለ ቴዎድሮስ ..... ፴፩
ጉራጌ ፤ ፵፪ ፤ ፹፩ ፤ ፻፴፱ ፤ ፻፺፩ ፤ ፫፻፯ ፤ ፬፻፳፯ ፤ ፬፻፵፰ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጊሪ (ጂሪ) ፤ ፪፻፬
ጊቤ ..... ፰፻፱
ጊኔ ....... ፻፵፫
ጊና አገር .... ፰፻፸፪
ጋምቢያ .... ፰፻ ፺፰
ጋዛ ..... ፺፰
ጋፋት ..... ፻፵፫ ፤ ፬፻፳፰ ፤ ፰፻፴፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ግድም ..... ፫፻፶፬
ግሪክ ፤ ፲፩ ፤ ፴፩ ፤ ፳፩ ፤ ፺፯ ፤ ፻፳፰ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ግሼን (አምባ ግሸን አምባ ነገሥት) ፤ ፲፫ ፤ ፵፫ ፤ ፬፻፶፫ ፤ ፬፻፷ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ግብፅ (ምድረ ግብፅ) ፤ ፰ ፤ ፳፫ ፤ ፳፬ ፤ ፴፰ ፤ ፻፳ ፤ ፻፲፪ ፤ ፻፴፫ ፤ ፻፴፬ ፤ ፻፴፯ ፤ ...
ብዙ ጊዜ
ግንደበሎ .... ፻ ፶፯ ፤ ፪፻፩ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጎንደር (ጎንደር) ፤ ፱ ፤ ፲ ፤ ፳፩ ፤ ፳፪ ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፸፰ ፤ ...... ብዙ ጊዜ
ጎዮኔ .... ፰፻፲፩
ጎጃም (ጎጃም) ፤ ፱ ፤ ፲ ፤ ፵፩ ፤ ፶፩ ፤ ፹፪ ፤ ፻፳፯ ፤ ፻፴፩ ፤ ፻፴፪ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጎአ (ጎአ) ፤ ፻፱ ፤ ፻፲፫ ፤ ፻፲፰ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፲፯ ፤ ፻፶፪ ፤ ...... ብዙ ጊዜ

ISIC

...ጠ...

ጠገዴ .... ፰፻፵
ጣና ሐይቅ (ጣና ባሕር) ፤ ፺ ፤ ፮፻፴፱ ፤ ..... ብዙ ጊዜ
ጣቁሳ ...... ፰፻፵
ጦቢያ ..... ፫፻፵፩

...ጨ...

ጨለቅላቃ .... ፪፻፴
ጨለቆት ...... ፬፻፸

...ጸ...

ጸለምት ፤ ፻፸፬ ፤ ፰፻፴፩ ፤ ፰፻፴፪ ፤ ....... ብዙ ጊዜ

...ፊ....

ፈረንሳዊ (ፈረንሳይ) ፤ ፳፰ ፤ ፶፯ ፤ ፺፯ ፤ .... ብዙ ጊዜ
ፈጠጋር (የዛሬው ቡልጋ ፤ ምንጃር) ፤ ፳፫ ፤ ፸፰ ፤ ፻ ፶፪ ፤ .... ብዙ ጊዜ

ፊንፊኔ ..... ፷፻፯

ፋርስ .... ፳፬ ፡ ፺፭ ፡ ፻፯ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፵፭ ፡ ..... ብዙ ጊዜ

ፍልስጥኤም ..... ፳፬


...ፐ...


ፓሪስ .... ፻፹፯

ፓለስቲን ፡ ፳፬ ፡ ፺፩ ፡ ፻፩ ፡ ፭፻፴፭ ፡ ....... ብዙ ጊዜ

ፖርቱጋል ፡ ፺፩ ፡ ፺፰ ፡ ፳፫ ፡ ፳፱ ፡ ፺፯ ፡ ፻፩ ፡ ፻፵፪ ፡ ..... ብዙ ጊዜ


## የማድፊት እርማት

| ተራ ቁጥር | ግድፈት | እርማት | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ይጸብአኒ | ይጽብዑኒ | 273 |
| ፪ | ወእመ ቅድመ | IS እምቅድመ | 301 |
| ፫ | ለተራድአትከ | ለተራድኦትከ | 431 |
| ፬ | ኖኅ መንግሥቱ | ኖኅ መንግሥቱ | 494 |
| ፭ | የጌታ ወታደር ወይም ጌታ የሚጠ ብቀው የሚለው | የጌታ ማኅደር ተብሎ እንዲነበብ ። | 527 |
| ፮ | ገጽ በገጽ | ገጸ - በገጽ | 560 |
| ፯ | በድባሒሃ | በጽባሒሃ | 641 |
| ፰ | እምዝ ነግሠ | እምዘነግሠ | 667 |
| ፱ | እለሰ ተርፋ ተዘርፉ | እለሰ ተርፉ ተዘርዉ | 688 |
| ፲ | ብዙኃ ዓመታት | ብዙኃ ዓመታተ | 694 |
| ፲፩ | እስከ ገልባቦ | እስከ ገልበቦ | 813 |

## ደራሲው ከዚህ በፊት ያሳተማቸው

፩ኛ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ ፪ ጊዜ የታተመ
፪ኛ " " አክሱም - ዛጉዬ ፪ ጊዜ የታተመ
፫ኛ " " ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ፪ ጊዜ የታተመ
፬ኛ " " ካፄ ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ቴዎድሮስ ፩ ጊዜ የታተ[illegible]
፭ኛ " " ካፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፫ ጊዜ የታተመ
፮ኛ የሰው ጠባይና አብሮ የመኖር ዘዴ
፯ኛ ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና
፰ኛ ጥንታዊት ኢትዮጵያና ግብፅ

ISIC